ወንጌል ቅዱስ

ዘእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።
የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ
ወንጌል ።

ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባብና
ትርጓሜው
(በአንድምታ)

ተኀትመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፲ቱ ወ፪ ዓመተ ሢመተ
ፓትርያርክናሁ ለብፁዕ ወቅዱስ አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ
ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት።

በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም
በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።
አዲስ አበባ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

መግለጫ፦

አርባዕቱ ወንጌላውያን

አበው "ቢቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል" እንዲሉ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሁለቱ ፥ ከሰብዓ አርድእት ሁለቱ በመንፈስ ቅዱስ ተመርጠው ቅዱስ ወንጌልን በመጻፋቸው አራቱ ወንጌላውያን ተብለው ተሰይመዋል ። እነሱም ቅዱስ ማቴዎስ ፥ ቅዱስ ማርቆስ ፥ ቅዱስ ሉቃስ ፥ ቅዱስ ዮሐንስ ናቸው ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ይደልዎ ለዘያነብብ ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዓለ መጽሐፍ ወእምዝ ይምሐር ወያንብብ" እንደ አለው (ተግሣጽ 8· ገጽ 99) ስለ አራቱ ወንጌሎች ከመጻፋችንና ከመናገራችን አስቀድሞ ስለ አራቱ ወንጌላውያን የሕይወት ታሪክ በአጭሩ ልንገልጽ እንወዳለን ።

1· ሀ/ ቅዱስ ማቴዎስ

በዕብራይስጥና በአረማይስጥ ቋንቋ ማቴዎስ ማለት ሀብተ እምላክ ፥ ወይም የእምላክ ስጦታ ማለት እንደ ሆነ ይነገራል። በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የስም ዝርዝር ውስጥ በሁለተኛውና በሦስተኛው ማለትም በማርቆስና በሉቃስ ወንጌል በተራ ቁጥር ሰባተኛ ሲሆን ስሙም ማቴዎስ በመባል ተመዝግቦአል ። (ማር፥ 3· 16–19 ፥ ሉቃ፥ 6· 14–16) ራሱ በጻፈው ወንጌልና በሐዋርያት ሥራ ደግሞ በተራ ቁጥር ስምንተኛ ሆኖ ማቴዎስ በመባል ተመዝግቦአል ። (ማቴ·10፡2–4 ፥ የሐ·ሥ·1፥13) __ሌዊ__ ለሐዋርያነት ከመመረጡ በፊት የተጠራበት ስሙ ሲሆን ማቴዎስ ደግሞ ለወንጌል አገልግሎት ለሐዋርያነት ከተጠራ በኋላ የተጠራበት ስሙ ነው ።

ለ/ የመጀመሪያ ሥራው

ቅዱስ ማቴዎስ ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ሥራው (ሊቀ መጸብሐን) ቀራጭ ነበር ። በሐዲስ ኪዳን የትምህርት አገላለጽ ቀራጮች እንደ አመንዝሮች ፥ ዓመፀኞች ሌቦች ይቆጠሩ ነበር ። (ሉቃ·18፥ 1 1–12) በዚህ አንጻር ማቴዎስ ቀራጭ እንደ መሆኑ መጠን የዘመኑ የሃይማኖት ሰዎች ይጠሉት ነበር ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማቴዎስን በመቅረጫው ቦታ አገኘውና "ተከተለኝ" በማለት ስለ ጠራው ሁሉን ትቶ ተከተለው። (ማቴ· 9፡9) ቀራጩ ማቴዎስ ሐዋርያና ወንጌላዊ ሆነ ፤ መደቡ ከአመንዝሮችና ከአመፀኞች ጋር የነበረነው __ሌዊ__ከአሥራ ሁለቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ ። ከአራቱ ወንጌሎች የመጀመሪያውን ወንጌል ጌታ ከአረገ ስምንተኛው ተፈጽሞ ዘጠነኛው ሲጀመር ፤ ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት በዕብራይስጥ ቋንቋ ጻፈ ።

ሐ/ ምልክቱ፦

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከአብርሃምና ከዳዊት ዘር መወለዱን ለማስረዳት ከአብርሃም እስከ ቅድስት ድንግል ማርያም ድረስ በሰፊው ስለጻፈ ከጥንት ጀምሮ ማቴዎስ በገጸ ሰብእ ተመስሎአል ። ከሦስቱ ወንጌላውያን ይልቅ በማቴዎስ ወንጌል ክርስቶስ ወልደ እጓለ እመሕያው ፥ የሰው ልጅ በመባል ብዙ ጊዜ ስለተጠራ ለማቴዎስ የገጸ ሰብእ ምልክት ከአሰጡት ምክንያቶች አንዱ ነው ።

2ኛ· ሀ/ ቅዱስ ማርቆስ

ቅዱስ ማርቆስ ሐዋርያና ወንጌላዊ ፥ እንደዚሁም ሰማዕት ነው ። ከዚህም ጋር የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሥራች አባት ነው ። ወንጌላዊው ቅ/ማርቆስ ኢየሩሳሌም ውስጥ ክርስቲያኖች በቤቷ ለጸሎትና ለትምህርት ይሰበሰቡ የነበረችው የማርያም ልጅ ሲሆን አባቱ አርስጦሉስ ፥ አጐቱ በርናባስ ነበሩ ። ቅዱሳን ሐዋርያት ሁል ጊዜ በእናቱ ቤት እየተሰበሰቡ ጸሎት በማድረግ ፈጣሪያቸውን ያመስግኑ ነበር ። (የሐ· 12፥12) እናቱ ማርያም እጅግ የከበረች ባለጸጋ እንደነበረችም በመጽሐፈ ስንክሳር ተጠቅሶአል ። ቅዱስ ማርቆስ በመጀመሪያ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራ ነበር እናቱም ልጇን ማርቆስን በዕብራይስጥና በዮናናውያን ቋንቋ እያስተማረች እንዳሳደገችው ይታመናል ። ቅዱስ ማርቆስ በወጣትነት ዘመኑ የጌታን ትምህርት ሰምቶ ልቡ ስለተነካ ሁሉንም ነገር ትቶ የክርስቶስን ወንጌል መንግሥተ ሰማያት ለመስበክ ቆርጦ ተነሳ ። ጌታ ካረገ በኋላ ቅዱስ ማርቆስ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በመሆን ወንጌልን በማስተማሩ ቅዱስ ጴጥሮስ ልጄ እያለ ይጠራዋል ። (1· ጴጥ፥5፥12) ከጌታ የሰማውንና የተማረውን ጽፎአል ። ወንጌሉም ከእሱ በኋላ በእሱ ስም ተጠርቶአል ። ወንጌሉን የጻፈበት ዘመን ጌታ ከዐረገ አሥራ አንደኛው ተፈጽሞ አሥራ ሁለተኛው ሲጀመር ፤ ቀላውዴዎስ ቄሳር በነገሠ በአራተኛው ዓመት ሲሆን የጻፈበትም ቋንቋ ሮማይስጥ ነው ።

ለ/ ምልክቱ፦

ቅ/ማርቆስ በአንበሳ ተመስሎአል ። ምክንያቱም አንበሳ በቅዱስ መጽሐፍ ለእግዚአብሔር ፥ ለሰዎችም

ምልክት እንደሆን ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል ። በኦሪት ዘፍጥረት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳና ከንጉሥ ዳዊት ዘር እንደሚወለድ ተተንብዮአል ። (49·9–10) በነቢዩ በሆሴዕ እግዚአብሔር አንበሳ ተብሎ መጠራቱን እናያለን (13፥7) መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አሸናፊው የይሁዳ አንበሳ ተብሎ መሰየሙን በራዕየ ዮሐንስ ተጽፎአል ። (5፥5) በአሶራውያንና በዕብራውያን ዘንድ በዙፋንና በበትረ መንግሥት ላይ የአንበሳ ምልክት ይሣል ነበር ። (1·ነገ፥7·29–36 ፥ 10· 19–20) ። ቅዱስ ማርቆስ በአንበሳ የተመሰለበት ዐቢይ ምክንያት ደግሞ በግብጽ የነበሩትን የአንበሳ ጣእታት በስብከቱ አጥፍቶ አንበሳ ዕጓለ አንበሳ የተባለውን ክርስቶስን በመስበኩ ነው ።

3ኛ· ሀ/ ቅዱስ ሉቃስ

ወንጌላዊው ሉቃስ አንጾኪያ ውስጥ የግሪክ ወገን ከሆኑ ቤተሰቦች ተወልደ ፤ ጌታ ካረገ በኋላም ቆይቶ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር አብሮ ወንጌልን እንዳስተማረ ተጠቅሶአል (2 ጢሞ፥ 4፥4) ሐኪምም እንደነበረ ተጽፎአል ቆላስይስ 4·14 ። በስሙ የሚጠራውን ወንጌልና የሐዋርያትን ሥራ የጻፈው ወንጌላዊው ሉቃስ ነው ። ጌታ ከሙታን ተለይቶ ሞትን ድል አድርጎ በተነሣበት ቀን በፍኖተ ኤማሑስ (በኤማሑስ መንገድ) ጌታችን ከተገለጸላቸው ከሁለቱ ደቀመዛሙርት አንዱ ቅዱስ ሉቃስ እንደሆነ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ያስተምራሉ ። (ሉቃስ 24· 13 –32) ። ወንጌሉንም የጻፈበት ዘመን ጌታ ከዐረገ ሃያ አንድ ዓመት ተፈጽሞ ሃያ ሁለተኛው ሲጀመር፤ ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በአሥራ አራተኛው ዓመት በዮናኒ ቋንቋ ነው ።

ለ/ ምልክቱ፥–

ወንጌላዊው ሉቃስ በላህም ይመሰላል ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከብቶች በረት መወለዱን ፥ በዕለተ ልደቱም የከብት አረኞች ከመላእክት ጋር መዘመራቸውን ከሌሎች ወንጌላውያን ሠፋ አድርጐ ስለሚተርክ ነው ። (ሉቃ፥ 2· 8–18) ከዚህም ሌላ ላህም በብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት እንስሳ ሲሆን ሉቃስም የክርስቶስን መስዋዕትነት በፍሪዳ ምሳሌ ጽፎአል ። (ሉቃ·15፥ 22–24) ላም የቀንድ ከብት ነው በዚሁ መሠረት ወንጌላዊው ሉቃስ ክርስቶስ ቀርነ መድኃኒት እንደሆነ ነቢዩ ዘካርያስ የተናገረውን ትንቢት በመግለጽ ስለጻፈ የላህም ምልክት እንደተሰጠው መተርጉማን ሊቃውንት ይናገራሉ ።

4ኛ· ሀ/ ወንጌላዊው ዮሐንስ

ጌታ ይወደው የነበረው የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ በፍልስጥኤም ከፍልስጥኤምም ውጪ ክርስትና እንድትስፋፋ ያደረገ ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ እመቤታችንን እንዲያገለግላት አደራ የተቀበለ የእመቤታችን የአደራ ልጅ የሆነ ነው ። (ዮሐ· 19፥26) ከዚህም ጋር ከቅዱስ ጳውሎስ ዕረፍት በኋላ ከኢየሩሳሌም ወደ ኤፌሶን ሄዶ በትንሿ እስያ ወንጌልን የሰበከ በሮማዊው ቄሣር በዶሚቴያኖስ ዘመነ መንግሥት ወደ ፍጥሞ ደሴት ተሰዶ በእስር ቤት ሳለ ራእይን የጻፈ ከዶሚቴያኖስ ሞት በኋላ ወደ ኤፌሶን ተመልሶ "ልጆቼ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ" እያለ ያስተማረ በስሙ የሚጠሩትን ወንጌሉን እና ሦስቱን መልዕክታት እንዲሁም ራዕይን የጻፈ ፥ ንባቤ መለኮት የሚል ስም የተሰጠው ሐዋርያ ነው ። ወንጌሉንም ጌታ ከዐረገ በሠላሳ ፥ (በሠላሳ አምስትም የሚሉ አሉ) ። ኔሮን ቄሣር በነገሠ በስምንት ዓመት በዮናኒ ቋንቋ ጻፈ ። በልሳን ጽርዕ የሚልም አብነት አለ።

ለ/ ምልክቱ፡–

ወንጌላዊው ዮሐንስ በንስር ተመስሏል ። በሥነ እንስሳት (አሞሮች) ጥናት ሊቃውንት እንደሚነገረው ንስር ከሌሎች አዕዋፍ ሁሉ ተለይቶ ወደላይ መጥቆ ይበራል ። በላይም ሆኖ በመሬት ላይ ያሉትን ረቂቃን ነገሮችን አጣርቶ መመልከት ይችላል ። ወንጌላዊው ዮሐንስም ወንጌሉን ሲጽፍ ከወንጌላውያኑ እጻጻፍ በተለየ በምሥጢረ ሥላሴ ይጀምራል ፥ ስለሥጋዌም ሲጽፍ ወደላይ መጥቆ በማሰብ ቅድመ ዓለም ስለነበረው ቃል ይተርክና "ያ ቀድሞ የነበረው ቃል ሥጋ ሆነ" በማለት ይጽፋል (ዮሐ· 1፥14) ። ንስር ወደላይ እጅግ መጥቆ እንደሚበርና ወደምድር ሲመለከት ረቂቃን የሆኑትን ነገሮች መመልከት እንደሚችል ፥ ዮሐንስም ረቂቅና ጥልቅ የሆነውን ትምህርት ያስተምር ነበር ። እነዚህም ፥ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" ፥ "እግዚአብሔር ብርሃን ነው" ፥ "ክርስቶስ ሕይወት ነው" የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው ።

ስለዚህ ከቀድሞ አባቶቻችን ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ ከእኛ የደረሰውን የአራቱን ወንጌሎች የአንድምታ ትርጓሜ መምህራን እንዲያስተምሩበት ፥ ደቀመዛሙርት እንዲማሩበት ፥ ምእመናን እምነታቸውን በስፋትና በጥልቀት እንዲረዱበት ቢያቀርብ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማዋል ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ።

ታሪክ

ይህን መጽሐፍ አሞንዮስ አውሳብዮስ ተናግረውታል። እነዚህስ መነሻታቸው ከሥለስቱ ምእት በፊት ነውን ወይስ በኋላ ቢሉ በፊት ነው።ይህ በምን ይታወቃል ቢሉ ከሥለስቱ ምእት በኋላ የተነሡ ሊቃውንት ከመዝ ይቤሉ አበዊነ ከመዝ ይቤሉ እጋእዝቲነ ከመዝ ይቤሉ መምሕራኒነ እያሉ ሠለስቱ ምእትን ያነሣሉ እሊህ ባለማንሣታቸው።ያስ ከሥለስቱ ምእት በኋላ የተነሡ ሊቃውንት እንዲህ እያሉ ሠለስቱ ምእትን ማንሣታቸው ለሃይማኖት ሲከራከሩ ጉባኤ ሲያቆሙ ነው። እኒህ አለማንሣታቸው በሃይማኖት ባይከራከሩ ጉባኤ ባያቆሙ ነው። መነሻታቸውም ከሥለስቱ ምእት በኋላ ነው። ይህን ስለ ስድስት ነገር ተናግረውታል። መጀመሪያውን ግብር ተዳግሮ ብለውታል ግብር ተዳግሮ ይባላል። ለአሪት ግብር አላት።በተዳግሞ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ትላለች ለወንጌል ምን ግብር አላት እንዳይሉ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ሰው እንደሆነ ትናገራለችና ይህን ለመናገር ወካልኡ በቍዔት ይላል። ፪ተኛውን በቍዔት ብለውታል በቍዔት ይባላል ለአሪት በቍዔት አላት ፳ኤል ፪፻ ከ፲፭ ዘመን ኑረው ከግብፅ እንደወጡ ትናገራለች ለወንጌል ምን በቍዔት አላት እንዳይሉ ነፍሳት ፭ሺህ ፭፻ ዘመን በገሃነም ኑረው እንደወጡ ትናገራለችና ይህን ለመናገር ወሣልሱ ሥርዓት ይላል፣ሶስተኛውን ሥርዓት ብለውታል ሥርዓት ይባላል፣ለአሪት ሥርዓት አላት እመኒ እንዘ ትነውም ወእመኒ እንዘ ትነቅሕ እመኒ እንዘ ትነብር ወእመኒ እንዘ ትትነሣእ፣እመኒ እንዘ ትቀውም ወእመኒ እንዘ ተሐውር ኢትርሣእ ተዘክሮተ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ትላለች፤ለወንጌል ምን ሥርዓት አላት እንዳይሉ ይእቲኬ አንብቦቱ በኵሉ ጊዜ ትላለችና ይህን ለመናገር፣ወራብዑ ስም ይላል ፬ተኛውን ስም ብለውታል ስም ይባላል፣ለአሪት ስም አላት አሪት ትባላለች፤ለወንጌል ምን ስም አላት እንዳይሉ ወንጌል ትባላለችና ይህን ለመናገር፣ወኃምሱ መሠረት ይላል፣አምስተኛውን መሠረት ብለውታል መሠረት ይባላል፣ለአሪት መሠረት አላት አስገኝዋ ጌታ ጸሐፊዋ ሙሴ እንደሆነ ትናገራለች ለወንጌል ምን መሠረት አላት እንዳይሉ አስገኝዋ ጌታ እንደሆነ አራት ጸሐፍት እንደጻፏት ትናገራለችና ይህን ለመናገር፣ወሳድሱ ምስማክ ይላል ስድስተኛውን ምስማክ ብለውታል ምስማክ ይባላል ለአሪት ምስማክ አላት ለእመ ዓቀብከ አሪተከ ትበልዕ ከራሜ ከራሚከ ወይሰናፍ ማኅበብተ ወይንከ ወትሬኢ ውሉደ ውሉድከ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ትላለች፣ለወንጌል ምን ምስማክ አላት እንዳይሉ ከአርአያ እግዚአብሔር አሰጥታ ታከብራለችና ይህን ለመናገር፣ወሳብኡ እርእስተ ነገር ይላል ሰባተኛውን ክፍለ ነገር ብለውታል ክፍለ ነገር ይባላል፣ለአሪት ክፍል አላት አራት ወገን ሁና ተጽፋለች፤ለወንጌል ምን ክፍል አላት እንዳይሉ አራት ወገን ሁና ተጽፋለችና ይህን ለመናገር፣ይህ አንድ ወገን ነው፣ሁለተኛ ባዲራሽ ገብቶ ወይ እልፍኝ ማለፍ እርከብ ተረግጦ ወይክርቻ መውጣት እንዲመች መቅድሙን ተምሮ ወይወንጌል ሲገቡ ይመቻልና።ከማያውቁት አገር የሚያውቁትን ሰው ሲያገኙት ደስ እንዲያሰኝ፣መቅድሙን ተምሮ ወይወንጌል ሲገቡ ደስ ያሰኛልና፣፪ቱን አንድ ወገን አድርገህ ፪ት በል።ሶስተኛም ለመጻሕፍት መልክ ለመስጠት ዓቢዩን በቀይ፣ንዑሱን በጥቁር፣ዘሩን በ ነጥብ ለመለየት፣ሐዋርያት በዘላን አሞንዮስ አውሳብዮስ በቋሚ ይመስላሉ፣ዘላን ላሙን ነድቶ አምጥቶ አስረክቦ ይሄዳል እንጂ ላሙን እርዶ ሥጋውን አወራርዶ ይህ ብልት ይህ ነው ብሎ አያስረክብም ቋሚ ግን ከዘላን ተቀብሎ ላሙን እርዶ ሥጋውን አወራርዶ ይህ ብልት ይህ ነው ብሎ ለና

ር ቶጽር ያስረክበል እንዳይሠረቅ።ዘላን ላሙን ነድቶ አምጥቶ እንዳያስረክብ ሐዋርያትም አራት አድርገው ጻፉ እንጂ ይህን ያህል ዓቢይ ምሰራፍ ይህን ያህል ንዑስ ምዕራፍ ይህን ያህል ዘር ብለው አልጻፉም፤ቋሚ ከዘላን ተቀብሎ ላሙን እርዶ ሥጋውን አወራርዶ ይህ ብልት ይህ ነው ብሎ ሰፍሮ ቆጽሮ እንዳያስረክብ እንዳይሠረቅ፤እሞንዮስ አውሳብዮስም ይህን ያህል ዓቢይ ምዕራፍ ይህን ያህል ንዑስ ምዕራፍ ይህን ያህል ዘር ብለው ደጽፈሉና ስለዚህ ሐዋርያት በዘላን እሞንዮስ አውሳብዮስ በቋሚ ይመሰላሉ።

በስመ አብ ።

በአብ ስም አምነን አብን ወላዲ ብለን ።

ወወልድ ።

በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን ።

ወመንፈስ ቅዱስ ።

በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብለን ።

፩አምላክ ዘለዓለም ።

ምንም ለአጠይቆ አካላት ሶስት ብንል በባሕርይ በሕልውና አንድ አምላክ ብለን አምነን ንቀድም ። አንድም አብን በልብ ወልድን በቃል መንፈስ ቅዱስን በእስትንፋስ መስለን፤በባሕርይ በሕልውና አንድ አምላክ ብለን አምነን ።

ንቀድም በረድኤተ እግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር አጋዥነት እንጀምራለን ።

ሐተታ እግዚአብሔርን አጋዥ ካላደረጉ እማር እስተምር አነብ እተረጉም አጽፍ እደጉስ ቢሉ አይቻልምና ዣላኬ ፍድፋዴ እንተ ይገብሬ ብእሲ ኢትትፌጸም ዘእንበለ በረድኤተ እግዚአብሔር በከመ ቃሉ ለእግዚእነ ወዘእንበሌየሰ አልቦ ዘትክሉ ገቢረ ወኢምንትኒ እንዲል ። አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዘለዓለም ። አሐዱ ዘለዓለም አምላክ ዘለዓለም ብለህ ግጠም ። አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዘለዓለም አለ በሶስትነታቸው ርባዔ የለባቸውምና ። አሐዱ ዘለዓለም አለ በአንድነታቸው ምንታዌ የለባቸውምና ። አምላክ ዘለዓለም አለ ከዚህ ዓለም ንጉሥ ሲለይ ። የዚህ ዓለም ንጉሥ እንዲ ሲያልፍ እንዲ ሊተርፍ ነው ። ሥላሴ ግን ቅድመ ዓለም ማዕከለ ዓለም ድኅረ ዓለም ንጉሥ ናቸውና ። ሎቱ ስብሐት ። ክብር ይገባውና ይትባረክ ስሙ ።

ስሙ ይክበር ይመስገንና ።

ወይትለዓል ዝክሩ ።

በልብ መታሰቡ በቃል መነገሩ ከፍ ከፍ ይበልና ።

ወፍጽምናሁ ።

ሕልውናው አንድነቱ ከፍ ከፍ ይበልና ።

ዘእምኔሁ ሚመተ ኵሉ ኃይል ።

የመላእክት ሹመት ከሱ የሚገኝ።ሠያምያነ መላእክት ኀራን እንዲል ። እንዲሁም የቀሳውስት ሹመት ከሱ የሚገኝ።ወውእቱ ዘይሠይሞሙ ለሰብእ ዛቲ ማዕርግ እንዲል ።እንድም የነገሥታት የመኳንንት ሹመት ከሱ የሚገኝ።እእምር ከመ ልዑል ይኴንን መንግሥተ ደቂቀ እጓለ እመሕያው ወለዘፈቀደ ይሁብ እስመ ኢይሰየም መኰንን ዘእንበለ እምኀበ እግዚአብሔር እንዲል ።

ወበቱ ተፍጻሜተ ኵሉ ስዕለት ።

የልመና ሁሉ ፍጻሜ በሱ የሚሆን ወኢይትከሃል ያቅርቡ ወኢምንተኒ ዘእንበለ በአራቅያናሁ ለወልድ እንዲል ።

ወኀቤሁ ምብጻሐ ኵሉ አስተብቍዖት ።

የምልጃ ሁሉ መዳረሻ ወደሱ የሚሆን ። ሐተታ ጻድቃን መላእክት ቢያማልዱ ፍጻሜው ወደሱ ነውና ። ስዕለት አስተብቍዖት የሚለው እንደምን ነው ቢሉ ስዕለት የሚለው በሰባቱ በዐሥራ ሁለቱ በሃያ አራቱ ጊዜያት የሚጸለየው ነው አስተብቍዖት የሚለው ሰው ስለሚሻው ነገር ግብር ገብቶ ቀኖና ይዞ የሚያመለክተው ነው ።

በጽሒፈ መቅድመ አርባዕቱ ወንጌላት ቅዱሳት ።

ንቀድም ጽሒፈ በ በግዕዝ ቦታ የገባ ነው አንተሰ ኢቀባዕከኒ በዘይት ርእስየ ስምዑራን ልብ በጥበብ ። ቀስተ ዮናታን ኢተቀብዓት በቅብዕ ዘእንበለ በደመ ኃያላን ። አራት ወንጌላት ወወንጌል ሰበኩ በክርስቶስ እንዲል ። የአራቱ ወንጌል መቅድም ሰባቱን ክፍል መጻፍን እንጀምራለን ። አንድም በን ስለ ማውጣት በመጻፍ እንጀምራለን በቃል መጀመር አለና ። አንድም ወታቀንተኒ ኃይለ በጸብዕ እንዲል በጽሑፍ ጌዜ ረድኤተ እግዚአብሔርን መጠጋትን ለነገራችን ተግ እናደርጋለን ።

ወአሠርቱ አቅማራት ።

ዐሥሩን ስንጠረዥ መጻፍንም እንጀምራለን፡አንድም ስንጠረዥን መቅድም አድርግ ፤ የአራቱ ወንጌል መቅድም የሚሆን ዐሥሩ ስንጠረዥ መጻፍን እንጀምራለን ፤ አንድም ጽሒፍን አውርድ ፤ ጽሒፈ መቅድመ ፲ቱ አቅማራት ፤ የዐሥሩ ስንጠረዥ መቅድም የሚሆን ሰባቱን ክፍል መጻፍን እንጀምራለን ሐተታ ምኑናት መጻሕፍተ ዕዳ መጻሕፍተ ደብዳቤ አሉና ከዚያ ሲለይ ከቡራት አሉ ፤ ርኩሳት መጻሕፍተ ጥንቆላ አሉና ከዚያ ሲለይ ንጹሐት አለ በበሳመ እግዚአብሔር አብ አሜን ።

እግዚአብሔር አንድ ቢያደርገን ፤ ሐተታ አእላፈ እስራኤል አንድ ቢያደርጋቸው ንሴብሖ እንዳሉ፣ ሠለስቱ ምእት ሊቃውንት ነአምን በ፩ዱ ፣ አምላክ እንዳሉ ።
ወእምድኅረ ዝንቱ ፤

በሰላመ እግዚአብሔር አብ ብሎ ነበርና እግዚአብሔር አብ አንድ ካደረገን በኋላ፣ አንድም ንቀድም በረድኤተ እግዚአብሔር ብሎ ነበርና በእግዚአብሔር አጋዥነት ከጀመርን በኋላ፤አንድም በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብሎ ነበርና በሦስቱ ስም ካመንን በኋላ ።

ይሜኒ ዘይቀድም መቅድመ ነገር ፍሡሕ ፤
ዘይቀድምና መቅድም አንድ ወገን ፤ ነገር ወንጌል ናት ፣ ሥነ ዜና ለዘለዓለም እንዲል ፤ ፍሡሕ እሳት መጸድቃንስ ውስተ ሕይወት ዘለዓለም ትሳለችና ፤ የወንጌልን መቅድም መጻፍ ይመቻል ፤ አንድም እየራሱ ለማውጣት የወንጌልን የመቅድሙን መቅድም መጻፍ ይመቻል ።

[illegible] ሶቱ እንብቦቱ ርቱዕ ።

[illegible] [illegible] የሚገለጽበት ።

እኮቴት ለእግዚአብሔር ።
ክብር ይገባውና ።   ስዋሪ

ባሕርዩን በባሕርዩ የሚሰውር ሰውር ብከ ዕበይከ ለሊከ [illegible] ተከደንከ ወሰሊከ ኪያከ አንጦላዕከ እንዲል፣ አንድም ቅዱሳንን በክብር የሚሰውር ወይሰውር ኅሩያን በደመና እንዲል ፣ አንድም ጻድቃንን ከመከራ የሚሰውር እስመ ሰወርከኒ ወረዳእከኒ እንዲል ።   ወከዳኒ ።

በንፍስ በሥጋ ከባቴ አበሳ ።

ነባቢ ፣   ቃል ።   ወከሃሊ
እካላዊ ፣ አንድም ነባቢ፣ ለይኩን ለይኩን ብሎ የተናገረ ፣ ወከሃሊ፣ያንኑ ማድረግ የተቻለው ሐተታ እሱ ተናግሮት ሳይደረግ የቀረ የለምና ወእምከመ ወጽአ ቃል ይትገበር ግብር እንዲል፣አንድም ነባቢ እወርዳለሁ እወለዳለሁ ብሎ ያናገረ ፣ ወከሃሊ ያንኑ ማድረግ የተቻለው ። አንድም ነባቢ ለማይ ወምድር የኅልፍ ብሎ የተናገረ ወከሃሊ ያንኑ ማድረግ የሚቻለው ።   ሕያው ።

ሕያው ለራሱ ፣   ወማኅየዊ ።
ማኅየዊ ለሌላው ፣   ወመዋኢ ።

መዋኤ ኃጢአት እስመ ንጹሐት ጠባይዓቲሁ ለእግዚአብሔር ዘእንበለ ነውር እንዲል ፣ አንድም መዋኤ ሥርዓት ወያፈልስ ሥርዓተ ውስተ ሥርዓት እንዲል እምሥርዓትም ይላል ። አንድም መዋኤ ሕሊናት እስመ ሕሊና ይደክም ወየሐጽር እምአእምሮተ እግዚአብሔር እንዲል ።

ዘእንቅሐ አልባቢነ ኀበ ዝክሩ ።
በልብ ወደመታሰቡ በቃል ወደመነገሩ ልቡናችንን ያነቃቃ ፣
ወመርሐ ልሳናቲነ ኀበ እኮቴቱ ወስብሐቲሁ ።
እሱን ፈጽሞ ወደማመስገን እንደበታችንን መርቶ ያደረሰ ። እኮቴተ ስብሐቲሁ ይላል ጌትነቱንወደ ማመስገን እንደበታችንን መርቶ ያደረሰ ።

ንሴብሖ እንከ በእንተ ዘወሀበነ እምነ ሠናያት ኂሩቱ በቸርነቱ ከሚገኝ ከበጐ ነገር ወገን ስለሰጠን እናመስግነው ። ሐተታ ሠናያት ያለው ልጅነት ነው ሀብትኬ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ እንዲል ።

ወናዕኵቶ እንበይነ ዘጸገወነ እምዕበየ ጸጋቲሁ ፣ በሊጋስነቱ ከሚሰጠው ክብር ወገን ስለሰጠን እናመስግነው ፣ ዕበየ ጸጋ ያለው ልጅነትን ግንዘብ አድርጎ [illegible] ከሞት እሳት ያለው ማዕርግ ነው ።

ወንቀድስ ስሞ ክቡረ ቅድሶተ ድልወ ።
ክቡር ስሙን የሚገባ ምስጋና እናመስግነው ። ሐተታ ባንድነቱ ምንታዌ ፣ በሦስትነቱ ርባዔ ሳንቀላቅል ። አንድም ሰውን ጻድቅ ቢሉት ሐሰት ። ባዕል ቢሉት ንዴት ፣ ኃያል ቢሉት ድካም ፣ ይስማማዋል እሱ ግን ጻድቅ ዘአልቦ ሐሰት ፣ ባዕል ዘአልቦ ንዴት ኃያል ዘአልቦ ድካም ነውና ።

በእንተ ዘከሠተ ለነ እምነ ምሥጢራተ ሃይማኖት በተዋሕዶተ ባሕርዩ ለሊሁ ።

ከሠተ ለሊሁ በባሕርይ አንድ መሆኑን ከማመን ምስጢር ወገን ስለገለጸልን እናመስግነው ፣ ሐተታ በከፊል ተናገረ የወጣኒ የማዕከላዊ የፍጹም እለና በኑ እምነቶሙ ቆመ እምነተ አብርሃም እንዲል ።
ወትሥልስተ አካላቲሁ ።
በአካል ሦስት መሆኑን ።   ወገጻቲሁ
በቅርጽ ፣   ወመልክዑ ፣   በገጽ ፣   ወአሳሬሁ
አንድ አድራጊውን ከማመን ምሥጢር ወገን ስለገለጸልን እናመስግነው ወአስረ ፪ቱ ሕላዌያተ እንዲል ወንስብሖ ስባሔ ፍጹመ ።

ፈጽመን እናመስግነው ።
በእንተ ዘወሀበነ ቦቱ ፤
ኪያሁ ሲል ነው አብ ቢሉ ልጁን ስለሰጠን ወልድ ቢሉ እካሉን ለተዋሕዶ ስለ ሰጠልን ሥጋውን ደሙን ስለ ሰጠን ፤

ወበእንተ ዘአፅተተ እምኔነ ኵሎ ምግባረ ዕልወታ በዘአምጽአ ቦቱ ውስተ ወንጌሉ ቅዱስ

ሰው ሁኖ በሠራት በወንጌል ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኃን ባለው ኢትጥዓምን ፤ ኢትልክፍን ስለአሳለፈልን ፤ እንድም አዳምና ሔዋን ያመጡትን ፍዳስ ለአራቀልን ፈጽመን እናመስግነው በግብራቸው ዕልወታት አላቸው ።

ወቦቱ አስተርአየት ተእምራቲሁ
ድውይ መፈወሱ
ወተከሥተት መንክራቲሁ ጋኔን ማውጣቱ
ወኃይላቲሁ
ሙት ማንሣቱ የተገለጸችበት
ወስብሐት ሎቱ ክብር ይግባውና
ይዕበይ ክብሩ
ጌትነቱ ይክበር ይመስገንና
ወይትለዓል ዝክሩ
በልብ መታሰቡ በቃል መነገሩ ከፍ ከፍ ይበልና
ወፍጽምናሁ
ሕልውናው አንድነቱ ከፍ ከፍ ይበልና

ወምስለ ዝንቱ ኵሉ ከመ እስትጉቡእ ዘይትፈቀድ ኀበ ጥያቄሃ ወፈቂድ ኀቤሃ ውስተ ኵሉ መጽሐፍ ጂቱ ይህም ይህ ነው ከዚህ ጋራ በዚህ ላይ እሷን ከሹዋት ከመረመሯት ዘንድ ልቡና የሚሻው ነገር ሁሉ እንደ ተሰበሰበ ሁኖ አለ ፤ ጸሙዓተኒ ማንሻ ። እንድም ይህም ይህ ነው ከዚህ ጋራ በዚህ ላይ እሷን ከሹዋት ከመረመሯት ዘንድ ልቡና የሚሻው ነገር ሁሉ በሰባቱ ክፍል እንደተሰበሰበ ሁኖ እሷን በጽፈት ወደመሻት ወደማሰብ ማለት እሷን ወደመጻፍ ወናሁ ጸውዐተኒ መፍቅድ ኀበ ኃሢሥ ዘከሮታ ። እሷን በጽሕፈት ወደመሻት ወደማሰብ ፈቃድ ንጉሥ ፈቃደ ነፍስ ፈቃደ መንፈስ ቅዱስ አነሣሣችኝ መፍቅድ ዐፀባ ይላል አብነት ቁርጽ ፈቃድ ፤ የላይ ቤት አማርኛ እገባሪ ፈቃድ ።

ወጽሕፈቱ ውስተ ዝንቱ መጽሐፍ ንጹሕ ከመ ይኩን ብጽሐቱ ስረባሕ ።

ዘፈቃደ ሥጋ ንጹሕ ዘሚሆን በወንጌል እጠገብ ይህ መቅድም መጻፉ ለወንጌል መዳረሻ ሊሆን ነው ሐተታ ። ይህማ በሌላ ተጽፎ ተምረውት ቢገቡ ይክሊክልናልን ብሎ ፤ ጽሕፈቱ በዝንቱ ፤ ከፈቃደ ሥጋ ንጹሕ የሚሆን የመቅድም መጻፍ ለወንጌል መዳረሻ ሊሆን ነው ።
ወመርሐ ለዘየኃሥሣ ዘይትፈቀድ ።
የሚወደደው የሚሻው ምሥጢር ለሚሻ ደቀ መዝሙር መርህ ሊሆን ነው ።
ወዛቲ ይእቲ ግብር ቀዳማዊ ።

ይህ ነው መጀመሪያውን ግብር ቀዳማዊ ብለውታል ግብር ቀዳማዊ ይባላል ።
ወካልዑ በቁዔት ።

ሁለተኛውን በቁዔት ብለውታል በቁዔት ይባላል ወዳግሙ ይላል ።

ወሣልሱ ሥርዓት
ሦስተኛውን ሥርዓት ብለውታል ሥርዓት ይባላል
ወራብዑ ስም
አራተኛውን ስም ብለውታል ስም ይባላል ፤ ስምዮት ትእምርት ይላል አብነት ።
ወኃምሱ መሠረት ።

አምስተኛውን መሠረት ብለውታል መሠረት ይባላል እምአይቴ ይላል አብነት ።
ወሳድሱ ምስማክ ።
ስድስተኛውን ምስማክ ብለውታል ምስማክ ይባላል
ወሳብዑ እርእስተ ነገር ።
ሰባተኛውን ክፍለ ነገር ብለውታል ክፍለ ነገር ይባላል ።
ግብር ቀዳማዊ ።
መጀመሪያውን ግብር ቀዳማዊ ብለውታል ግብር ቀዳማዊ ይባላል ፤ እያይዞ ለመንገር ደገመው ።
ወግብሩሰ ለዝንቱ መጽሐፍ ማሕየዊ ።
ማሕየዊ የሚሆን የዚህ የመጽሐፍ ሥራው ።
ከመ ይርባሕ ቦቱ ሕይወተ ሕይወት ዘለዓለም ለደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ።
ጌታ ለደቂቀ ዕጓለ እመሕያው የዘለዓለም ድኅነትን ያስገኘበት ዘንድ ፤ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው የዘለዓለም ድኅንነትን ያገኙበት ዘንድ ነው ፤ ለደቂቀ ዕጓለ እመሕያው የዘለዓለም ድኅነት ይገኝበት ዘንድ ነው ፤
ወበጺሖቶሙ ኀበ ፈጣሪሆሙ ።
ወደፈጣሪያቸው መድረሳቸውን ፤ ተላጽቀቶሙ ከፈጣሪያቸው ጋራ አንድ መሆናቸውን ፤ ተመስሎቶሙ ፈጣሪያቸውን መምሰልን ያገኙበት ዘንድ ነው ፤ ሁሉንም ያስተረጕማል ።
በቃል ፤ ባነጋገር ፤
ወበምግባር ።
በሥራ ሁለት አርእስት ተናገረ ለሁለቱም ያመጣል በቃልስ እስመ ውእቱ ይጼውዕ ወይስሕብ ኀበ እእሮተ እግዚአብሔር ።
በቃል ያልሁት እግዚአብሔርን ወደማወቅ ያደርሳልና ስለዚህ ነው ።
ይትባረክ ። ይክበር ይመስገንና ።
ወይትለዓል ዝክሩ ።
በልብ መታሰቡ በቃል መነገሩ ከፍ ከፍ ይበልና በተዋሕዶተ ባሕርዩ ።

በባሕርይ አንድ መሆኑን ።
ወመለኮቱ ።
በአገዛዝ በጌትነት አንድ መሆኑን ።
ወትሥልስተ አካላቲሁ ።
በአካል ሦስት መሆኑን ።
ወገጻቲሁ ። በገጽ ።
ወመልክኡ ። በቅርጽ ሦስት መሆኑን ።
ወእገሪሁ ።
አንድ አድራጊውን ወደማወቅ ያደርሳልና ስለዚህ ነው ፡ ወእመረ ፫ቱ ህላዌያተ እንዲል ።
ወያጤይቅ ተሥጉተ ፩ዱ ሕላዌ እም፫ቱ ሕላዌያት ከሦስቱ አካላት የአንዱን አካል ሰው መሆኑን ያስረዳልና ስለዚህ ነው ።
ወተዋሕዶቶ በዘተሰብአ ቦቱ ።
ከተዋሐደው ሥጋ ጋራ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን ያስረዳልና ስለዚህ ነው
ወይዜኑ ኀዳጠ በተሐውሶቱ ወበአንሶስዎቱ ውስተ ዓለም እምጊዜ ልደቱ እምቅድስት ድንግል ንጽሕት እስከ ጊዜ ተንሥአቱ ወዕርገቱ ውስተ ሰማያት ንጽሕት ከምትሆን ከእመቤታችን ከተወለደ ዠምሮ እስከሚነሣበት እስከሚያርግበት ድረስ በዚህ ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመት ከአራት ወር ከዐሥር ቀን መኖሩን ያስረዳልና ስለዚህ ነው ።
ወበምግባርሰ ፤
ቃል ላለው ጨርሶ ምግባር ላለው እመጣ በምግባርም ያልሁት ።
እስመ በትግሣጻቲሁ ልዕልት ይወስድ ኀበ ምግባራት ሠናያት ወፍጹማት ወመሥመርያት ።
አንሰ እብለክሙ ባለው ፍጹማት ወደሚሆኑ ምግባራት ያደርሳልና ስለዚህ ነው ።
ወያቅል ትርፍት ወክብርት ።

ፍጽምት ክብርት ወደምትሆን ወደገድለ ልቡና ያደርሳልና ስለዚህ ነው ።

ወበኪዳኑ እንተ ጸርሐ ባቲ ወይቤ እመቦ ዘዐቀበ ቃልየ ይገብር ግብረ ዚአነ እገብር ወዘየዓቢ እምኔሁ ይገብር ።

እመቦ ዘዓቀበ ቃልየ ባለው ወበአስፍዎተ ኪዳኑ ይላል አብነት በወንጌል እመቦ ዘዓቀበ ቃልየ ባለው ያደርሳልና ስለዚህ ነው ።

ወዓዲ ትከውኖ ሕይወተ ዘለዓለም ፤
ዳግመኛ በዚህ ዓለም ብቻ ተአምራት አድርጋለት እንደ ጋን መብራት ሁናበት አትቀርም በወዲያው ዓለም የዘለዓለም ድኅነትዋ ታሰጠዋለች ።
ወትከውኖትሰ ፤
በዚህ ዓለም ብቻ ተአምራት አድርጋለት እንደ ጋን መብራት ሁናበት እንዳትቀር በወዲያውም ዓለም የዘለዓለም ድኅነትን እንድታሰጠው የሚያስታውቅ የሚያስረዳ ነገር ።

ላዕለ እለ ገብሩ ትእዛዞ አስተርአየት ላዕለ እደዊሆሙ ተአምራት ወመንክራት ወኃያላት ዓቢያት ፤ ላዕለ እደዊሆሙ ለእለ ገብሩ ትእዛዞ ፤ ሕጉን በፈጸሙ በሕጉ በጸኑ በሐዋርያት ቃል በሐዋርያት ሥልጣን ጋኔን ማውጣት ሙት ማንሣት ተደረገ ።
እስከ ውእቶሙ ከሠቱ አዕይንተ ዕውራን ፡

ዕውራንን እስከ ማብራት ደርሰው ፡ እስመ ፡ ውእቶሙ ከሠቱ ዕውራን ፡ ዕውራንን አብርተዋልና ፡
ወአንጽሑ እለ ለምጽ ፡

ልሙጻንን እስከማዳን ደርሰው አድነዋልና ።
ወሞእዎ ለሞት ።

ሞትን ድል እስከ መንሳት ደርሰው ድል ነስተውታልና ፡ ሐተታ ሞእዎ አለ ቢያም ይፈውሱበታል ቢገድል ያሥነሡበታል ኃጢአት ቢያሠራ ስርየት ይሰጡበታልና ፡

ወከብረት ነፍሶሙ በውስተ ዓለማት ፪ኤቲ ዘዝየ ወዘከሐ ።

በውነታቸው በወዲህም በወዲያም ዓለም ከበረች ሐተታ ፡ በወዲህ እግልከት ተመስሉ ሰብአ ወወረዱ ኀቤነ ብለዋችዋል ፤ በወዲያውም ወሀሎ ይትዌሰኩ ሥነ በዲበ ሥን ይለዋል ።
ወእምፍርሃተ ቃሉ ርኅቁ ጻድቃን እምነ ምግባራት ምኑናት ወፍትወተ ዓለም ርኅቀት ጥቀ ።
ወይወድይዎሙ ውስተ እቶነ እሳት ያለውን ነገር ከመፍራት የተነሣ ጻድቃን ከዓለማዊ ግብር ፈጽመው ተከለከሉ ፡ አንድም ወበፍርሃተ ቃሉ አርኃቀ ይላል ። ወይወድይዎሙ ውስተ እቶነ እሳት ባለው ነገር ጌታ ጻድቃንን ከዓለማዊ ግብር ፈጽሞ ከለከለ አንድም ወፍርሃተ ቃሉ ይላል ፡ ወይወድይዎሙ ውስተ ፡ እቶነ እሳት ያለውን ነገር መፍራት ጻድቃንን ከዓለማዊ ግብር ፈጽማ ከለከለች ፡ አንድም ቃሉ ፡ ባለው ፡ በቃሉ ይላል ዕፄሁ ዘኢይነውም ወእሳቱ ዘኢይጠፍእ ያለውን ነገር ከመፍራት የተነሣ ጻድቃን ከዓለማዊ ግብር ፈጽመው ተከለከሉ ፤ አንድም እንዲህ ባለው ነገር ጌታ ጻድቃንን ፈጽሞ ከለከለ ፤ አንድም እንዲህ ያለውን ነገር መፍራት ጻድቃንን ከዓለማዊ ግብር ፈጽማ ከለከለች ፡
ወተግኅሡ እምነጽሮታ ወዘክሮታ ፡

በዓይን ከማየት በልብ ከማሰብ ፈጽመው ተከለከሉ ።
ወጸርየት አልባቢሆሙ ። ሰውነታቸው እንደ ፀሐየ ፊሳ ማሰት ፀሐይ እንደወደቀበት ዕንቍ ጸራችላቸው ።
ወተጠበበት ሕሊናሆሙ ።

ልቡናቸው ተራቀቀችላቸው ።

እስከ በጽሑ ኀበ ሥርዓት ዘመላእክት ፡
ወደ መላእክት እነዋወር እስኪደርሱ ድረስ
ወበተግሣጻቲሁ ፡ አንሰ እብለክሙ ባለው

ወበተካይዶቱ ፤ እመቦ ዘዓቀበ ቃልየ ባለው ወበነገሮቱ ፤
ወጻድቃንሰ ውስተ ሕይወት ዘለዓለም ፤
ረሰዮሙ ለደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ተመሳልያነ ኀበ ፈጣሪሆሙ ።
ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ፈጣሪያቸውን እንዲመስሉ ልጹቃን ፤ ከፈጣሪያቸው ጋራ አንድ እንዲሆኑ ። ብጹሐን ፤ ወደ ፈጣሪያቸው እንዲደርሱ አደረጋቸው ፤ ከመ ይግበሩ ምግባራቲሁ ወይረሱ መንግሥቶ ፤ ሥራውን ሠርተው ክብሩን ይወርሱ ዘንድ ።

፲ተኛ ጉባኤ ።

ወካልዑ በቍዔት ።

ሁለተኛውን በቍዔት ብለውታል በቍዔት ይባላል ወዳግሙ ይላል አብነት ፤
ወበቍዔተ ዝንቱ መጽሐፍ ንጹሕ ፤
ከፈቃደ ሥጋ ንጹሕ የሚሆን የዚህ መጽሐፍ በቍዔቱ በቍዔትነቱ ፤
ካዕበ እሰመ ውእቱ በዘይትነበብ እምኔሁ ያጤይቅ አጥርዮ መድኃኒቱ ለአዳም ።

በዘይትነበብ ካዕበ ፤ በቍዔት ካዕበ ፤ ያጤይቅ ካዕበ ብለህ ግጠም ፤ እሱ ሁለተኛ በሱ በሚነገረው ነገር ሁለተኛ የአዳምን ድኅነት ማግኘቱን ሁለተኛ ያስረዳልና ስለዚህ ነው ፤ አጥርዮ መድኃኒቱ ባለው ግብረ መድኃኒቱ ይላል አብነት ፤ የአዳምን የድኅነቱን ሥራ ያስረዳልና ስለዚህ ነው ።
ወዘርዑ ፤
የልጆቹንም ድኅነት ማግኘታቸውን ያስረዳልና ስለዚህ ነው ።
እምጼዋዌ ሰይጣን ርጉም ፤
ርጉም ከሚሆን ከሰይጣን ምርኮኝነት የአዳምን ድኅነት ማግኘቱን ልጆቹም ድኅነት ማግኘታቸውን የድኅነቱን ሥራ የድኅነታቸውን ሥራ ያስረዳልና ስለዚህ ነው ።

ወተፈድዮቶሙ ሀየንተ ኀጕለት ዕረፍተ ሠናየ ፤
ባስ ጉዳት ፈንታ በጐ ዕረፍት ማግኘታቸውን ፤ ዘከመ ተፈድዩ ፤ ብጐ ዕረፍትን እንዳገኙ ይናገራልና ስለዚህ ነው ፤ ዕረፍተ ሠናይተ ፤ ገነተ ሠናይተ ፍኖተ ሠናይተ ፤ ግዕዘ ሠናይተ ፤ ገድለ ሠናይተ ይላል አብነት ፤
ወዓርጉ እምጽናፈ ጽልመት ኀበ ብርሃነ ልዕልና
የሰው ዳርቻ እንዲሉ ፤ ልዩ ከሚሆን ጨለማ ዳርቻ ልዕልና ወዳለው ብርሃን መውጣታቸውን ፤ ዘከመ ዓርጉ ፤ እንደወጡ ይናገራልና ፤ ስለዚህ ነው ።
ሐተታ ፤ ልዩ ያለው የዚህ ዓለም ጭለማ በዓይነ ሥጋ ይታያል የወዲያው ግን ለዓይነ ነፍስ እንጂ ለዓይነ ሥጋ አይታይምና ።

ወፈግዑ በጣዕመ ፤ ግእዛን እምድኅረ ነበሩ በመሪር ኃዘን ግብርናት ፤

ለዲያብሎስ መገዛት ባመጣው በጽኑ ኃዘን ከኖሩ በኋላ ጣዕመ ግዕዛንን አግኝተው ተድላ እንዳደረጉ ይናገራልና ስለዚህ ነው ።

ወዘኮነሰ ከመ ዲያብሎስ ኮነ ሊቀ ዓቢየ በውስተ መላእክት ።

የሆነስ ሆነና ቀድሞ ዲያብሎስ ሊቀ መላእክት አጋዜ መንጦላዕት እንደ ነበረ በማኝ ልንገርህ ፤ ያል ተያያዘ ፤ እንድም ለዲያብሎስ መገዛት ባመጣው በጽኑ ኃዘን ከኖሩ በኋላ ጣዕመ ግእዛንን አግኝተው ተድላ ማድረጋቸው እንደምን ነው ትለኝ እንደሆነ የዚህስ ነገር ዲያብሎስ ቀድሞ ሊቀ መላእክት አጋዜ መንጦላእት እንደነበረ በማኝ ልንገርህ ። ወሶበ ተዓደወ እመካኑ በስሕተት ወወፅአ እምትእዛዘ ፈጣሪሁ ዘውሱን ሎቱ ።

በስሕተት ከቦታው በወጣ ጊዜ ፍጡር ነህ ቢሉት ፈጣሪ ነኝ ባለ ጊዜ ከተወሰነለት ከፈጣሪው ትእዛዝ ወጣ ማለት ቀድስ ቢሉት ቀድሱኝ አለ ወድቀ ማኘሻ ፤ እንድም ፍጡር ነህ ቢሉት ፈጣሪ ፤ ቀድስ ቢሉት ቀድሱኝ ባለጊዜ ።
ወድቀ እመንበሩ ።
ከሹመቱ ተሻረ ከልዕልናው ተዋረደ ።

ወወድቁ ምስሌሁ ኵሎሙ ሠራዊቱ እለ ገብሩ ፈቃዶ
ነህ ያሉት ሁሉ ከሱ ጋራ እንደሱ ወደቁ ፤
ወወድቀ ውስተ ምድር ከመ ይግበር ባቲ በከመ ፈቀደ በትዕቢቱ ወበትዝኅርቱ ።

በትዕቢቱ በትዝኅርቱ የወደደውን ያደርግባት ዘንድ ወደዚህ ዓለም ወደቀ ለመሐመድ ልጁ መቃብር ሊባርከለት መካ እስጥንቡል ወደቀ
ታሪክ ጌታ መላእክትን በነገድ መቶ በከተማ ዓሥር አድርጎ ፈጥሮ ተሰወራቸው ባሕርዩ ረቂቅ እንደሆነ ለማጠየቅ ካልሹኝም አልገኝም ሲል መላእክትም እእምሮ እላቸውና ተመራመሩ እምአይቴ መጻእነ ወመኑ ፈጠረነ ለሊነኑ እምኀበ ርእስነ ተፈጠርነ ወሚመ እምካልዕ ብለው ዲያብሎስን ከሁሉ አልቆት ፈጥሮት ነበርና ወደላይ ቢያይ ድምፅ አጣ ወደታች ቢያይ ሁሉ ከበታቹ ሁኖ አየ እኔ ፈጠርኋችሁ ልበላቸው ብሎ አሰበ አስቦም አልቀረ እኔ ፈጠርኋችሁ አላቸው ። መላእክትም በቦታ እንደሆነ እኛ ከበታቻችን ያሉትን አልፈጠርናቸው በምን ምክንያት ፈጠርኋችሁ ይለናል ፈጥረህ አሳየን እንበለው ብለው አሰቡ አሰበውም አልቀሩ በቦታ እንደሆነ እኛ ከበታቻችን ያሉትን አልፈጠርናቸው በምን ምክንያት ፈጠርኋችሁ ትለናለህ ፈጥረህ አሳየን አሉት ሊፈጥር እጁን ከእሳት አገባው ፈጀው ዋይ ብሎ ጮኸ ፈወሰው ። እፍ

እፎ አምላክ ቢሆን ነው እንጂ ውሳጣዊ አምላክግ ቢሆን ስትል ነው ባላለኝም ነበር ብሎ አሰበ ፤ ይህን ያሰበት ልቡን ተሰማው ፈጀው ዋይ ብሎ ጮኸ መላእክት ተናወጹ ይህ ስሑት ፍጥረት ፈጽሞ ሳያስታቸው ልገለጽላቸው ብሎ እሉ በማያይበት በምሥራቅ በኩል አንስ አቤ እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ብሎ የኅሑን ብርሃን ፈጠረላቸው የብርሃን ኀርፍ አፈሰሰላቸው እሱንም ተድኖ እፈጥራለሁ ብለህ እጅህን ከእሳት አግብተህ ፈጀህ ዋይ ብለህም ጮህህ ፈወስኩህ እፎኑ አምላክ ቢሆን ነው እንጂ ውሳጣዊ አምላክግ ቢሆን ምን ስትል ነው ባላለኝም ነበር አልኝኝ ብሎ ሁለተኛ ፈውስ ዛሬ ነገሥታት መኳንንት መላታቸውን በርጥብ ቁርበት ጠቅልለው ገደል እንዲጥሉ ባደረው ጭለማ አጕናፅፎ ከኢየሩሳሌም በግያሚት አውርዶ በኢዮር ካሉ መላእክት ያርቃታል እስከ ረቡዕ ከዚያ ይሰነብታል በዕለተ ሠሉስ የተፈጠሩ አዝርዕትን አትክልትን ዕፅዋትን አይቶ እንዲህ አድርጎ ፍጥረት ማከናወን ለዚህም እንጂ ፐር አንርለት ይሆናል አለ ።

ወደኸ እንደሆነ በዚህ ዓለም ላንርህ አለው ለእግዚአብሔርን ግን ነቡቶን አለው ፤ በዕለተ ረቡዕ ፀሐይ [illegible] ተፈጠሩ [illegible] [illegible] መላእክትና እንዲል ፤ [illegible] አመስግኑኝ ቤት ፤ አንሰ ዕደወ እምዝንቱ ሕሊና ፤ እኔ ከግመዳዊ ውዑእ ነኝ አላመሰግንም ይሆንላችሁስ እንደሆን እራተኛ አድርጋችሁ አመስግኑኝ አላቸው ሠራዊቱ እያዩዞ አራት አለቆች አሉት ፤ ከሚካኤል ከገብርኤል ዘንድ ላካቸው ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ቢሄዱ ምስቱ ለማያት እይመስሏትም እኛም ከውሸት በቀር ያገኘነው ነገር የለም ። ገዥ ነኝ የሚለውን ወግተን እጅ እናድርጋት ብሎ ላከ። ከት እይንተ ንጉሥ እንደገባ እብድ ውሻ አድርገው እብድ ውሻ አስመስለው ሰደዷትው ። መጥተው ነገሩት ሚካኤል ገብርኤል ቢኋችሁ በኔ ዘንድ ቁም ነገርን ናቸው እንደ ቀለም ጸጸ እሳት እንጂ እይደሉ ብሎ ሰልፍ ተነሣ እሱ እቀብ የወጣሁ ይመስለዋል ቁልቁል ይወርዳል ። ጕየ እግዚእ ምስለ አርያም ሰማዩን ጠቅሎ ተመለሰ ብሎ አዝምሮ ተመለሰ ። መላእክት ይህን ሰምተው ይህ ስሑት ፍጥረት እስከ መቼ ድረስ በፈጣሪው ሲታበይ ይኖራል ብለው ገጠሙት ድል አደረጋቸው ። ሁለተኛ ገጠሙት ድል አደረጋቸው ። ፈቃድህ ባይሆን ነውን ብለው አመለከቱ ። ፈቃድስ ፈቃዴ ነው ድል የሚነግበትን ግብር ታውቁ ብዬ ነው ብሎ የብርሃን ትእምርት መስቀል ሰጣቸው እሱን ባየ ጊዜ ከዚህ በታች ወርዷል ፤ ነው አይገባውም ያሉ አሉ ፤ ነው ብሎስ አይገባውም ማለት አይመችም ብሎ እኛም እንደሉ ነን ያሉ አሉ ፤ ከሱ በቀር ፈጣሪ ነኝ ያለም የለ ብሎ ነው ይገባዋል ያሉ አሉ ይሆን አይሆን ብለው የተጠራጠሩ አሉ ። ሳይመራመሩ የቀሩ አሉ ነው ይገባዋል ያሉ አብረውት ወርደዋል ፤ ይሆን አይሆን ብለው የተጠራጠሩ በዚህ ዓለም ቀርተዋል ሳይመራመሩ የቀሩ በአየር ቀርተዋል ክብር ይሁናቸው ብሎ እፎ ፈቀደ ኀበ ፈቀደ ።
ከወደደ ዘንድ እንደምን ወደደ ፤

እስመ ሥልጣኑ እንተ ተፈጥረት ምስሊሁ ኢተዓተተት እምኔሁ ።
ፍጡር እንደሆነ የሚያውቅባት በተፈጥሮ የተሰጠችው ግዕዛኑ አልተነሳችውምና ።
ወእምዝ ተከሥተ ሎቱ ድኀረ ክብረ መንበሩ እንተ ሀለወ ባቲ አምጣና ወክብራ ፤ አምጣና ወክብራ ለክብረ መንበሩ እንተ ሀለወ ባቲ ከሹመቱ ከተሻረ ከማዕርጉ ከልዕልናው ከተዋረደ በኋላ ቀድሞ የነበረባት የማዕርጉ ደግነት ተገለጸችለት ።

ወተዘከረ ፍሥሐ ወኃሤት እንተ ኮነ ይትፌሣሕ ባቲ ምስለ መላእክት ወሊቃናት ወሥልጣናት ሰማያውያን ፤

ስመ ነገድ ከመላእክት ጋራ ያደርገው የነበረውን ተድላ ደስታውን አሰበ ።

በብዙኃ ቃላቲሆሙ ወኀብረተ ዜማሆሙ ፤
በነገራቸው ብዛት በምስጋናቸው አንድነት ሐተታ የነገር ብዛት ቅዱስ ውዱስ ስቡሕ ዕሹት ሃሌ ሉያ ማለት ነው ይህ ሁሉ በምሥጢር አንድ ነው ።
ወዘይፈደፍድስ እምኔሃ ፍሥሐ ወኃሤት ልዕልተ ወምዕዝተ እንተ ታቄርብ ኀበ እግዚአብሔር ይትለዓል ዝከሩ ።

በልብ መታሰቡ በቃል መነገሩ ከፍ ከፍ ይበልና ይልቁንም ወደ እግዚአብሔር የምታደርስ ተመስጦ ነበረችው ያቺን አሰበ ። ሐተታ ተቀብቷል ቢሉ የቶመቸ አልተቀባም ቢሉ ቢጸና ።
ወዘረከቦሂ ድኀረ ውእቱ እምድቀታት ።
ከዚህ በኋላ ከድቀታት ወገን ያገኘውን አሰቦ ፤ ሐተታ ድቀታት ብሎ አበዛ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወደ ኢዮር ከኢዮር ወደዚህ ዓለም ከዚህም በታች አውርዶታልና ።

ወጽልመት እንተ ገልበበቶ ወበዓፅፉ ላዕሌሁ ፤
ከጸናችበት እሱም ከጸናባት ከድንቁርና ወገን ያገኘውን አሰቦ ድቀታት ባለው ዋዌ ፤ አንድም ለላይኛው ልዕልተ ምዕዝተ ባለው ዋዌ የጸናችበትን የጸናባትን ድንቁርናውን አሰቦ ፤
ወሀየንተ ብርሃን ዘመላእክት ትፍሥሕት በአርአያ ሰይጣናዊት ርኩሰት ።

ደስ ብኗቸው የሚኖሩ መላእክት ስላገኙት ብርሃን ፈንታ በምታጌይፍ ባላጋራንት መልክ እንዳለ ፀውቅ ፤
ወሐለየ በትዕቢቱ ወበትዝኅርቱ ወይቤ እስመ ይፈቅድ እግዚአብሔር እግብአትየ ከመ ያንብረኒ ኀበ ዘቀዳሚ ንብረትየ እንተ ተዓተተት እምኔየ ወእምእሊአየ ።
በትዕቢቱ በትኀዝርቱ አስቦ ወይም እንጂ ወይም አኮን ከኔ ከወገኖቼም ከተለየች ወደ ቀደመች ማዕርጌ ሊመልሰኝ ይወድ ይሆናል አለ ፥
ወአእመረ እግዚአብሔር ይትለዓል ዝከሩ ሕሊናሁ እኩየ ወትዕቢቶ ፥
በልብ መታሰቡ በቃል መነገሩ ከፍ ከፍ ይበልና ክፉ አሳቡን ትዕቢቱን ዐውቆ ፥
ወእፎ ኃደገ ምግባራተ ሠናያተ ።
በጐ ምግባራትን እንደተወ አውቆ ፥
እንተ ይእቲ ትሕትና ወየዋሃት ወድኂን እምኃጢአት ።
ምግባራት ሠናያት የተባሉም ትሕትና ወየዋሐት ድኂን እምኃጢአት ናቸው ። ሐተታ ትሕትና ባለፈው መጸጸት ። የዋሃት ከሚመጣው መጠበቅ ። ድኂን ለሁለቱም ነው ።

ዘለፎ እግዚአብሔር በፈጠረ ብእሲ ዝልፈት ክሡተ አዳምን በመፍጠሩ መዝለፍን ዘለፈው ማሳፈርን አሳፈረው ማስወተትን እሰቆተተው ።
በእሠንዮ ፍጥረቱ ለአዳም ።

አዳምን አክናውና በመፍጠሩ ፤ እንደ ብርጭቆ የሚያንጸበርቅ እንደ ጽጌያት የሚያሽበርቅ አድርጎ በመፍጠሩ ይህስ ቁም ነገር አይደለም ዕዋቂ አድርጎ በመፍጠሩ ፤

እስመ ውእቱ ለሐኮ እም፬ቱ ጠባይዕ ።
ከአራቱ ባሕርያት ፈጥሮታልና ።

ወይእቲ እሳት ወነፋስ ማይ ወመሬት ።
አራቱ ባሕርያት የተባሉ እሳት ነፋስ ማይ መሬት ናቸው ።

ሥጋ ዘፍጹም ቆሙ ።

ቁመቱ ድልድል የሚሆን አካሉ እንደ ድንክ እያጥር እንደ ረዓይት አይረዝም ።
ዘቦቱ ፪ቱ ኃይል ።

ሁለት ግብር ሁለት ባሕርይ ያለው አድርጎ በመፍጠሩ ።

ኃይለ ዘርዕ ። የዘር ግብር የዘር ባሕርይ ።
ወኃይለ እንስሳ ።
የደመ ነፍስ ግብር የደመ ነፍስ ባሕርይ ።
ወኃይለ በቈላትስ በሁከተ ነፍስ ይነውኅ ወይማስን የዘር ግብር የዘር ባሕርይ ነፋስ እየወዘወዘው ያድጋል ነፋስ እየወዘወዘው ይደርቃል ፈርሶ በሰብሶ ይቀራል ።

በከመ ዕውቅ ዝንቱ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ምድር ይህ በአራቱ ማዕዘን ታውቆ እንዳለ ።

ወኃይልሰ እንስሳዊት ህውከት ይእቲ በሥምረት የእንስሳ ግብር የእንስሳ ባሕርይ ልብሳ ልብሳ በማለት ፈቃድ የምትነሣሣ ናት ።
ወይእቲ ባ እምነ እእምሮ ።

ወለይእቲ ሲል ነው ለኗም ከዕውቀት ወገን አላት ወከፈላ ምክረ እምጥበብ ለሰገኖ እንዲል ።
ዛይእቲ እንስሳዊት ያቺውም እንስሳዊት ናት ወውስቴታ ይትረከብ ነጽሮ ።

በርሷም ማየት ይገኛል ፥ ሐተታ ማየት በሁሉ አለ ይልቁንም ጉጉት የባሕር ድመት በሌሊት ያያሉ ።
ወሰሚዕ ።
መስማት ይገኛል ። ሰሚዕ በሁሉ አለ ይልቁንም በቅሎ ንቁሕ ነው ።
ወጣዕም ።

ጣዕም ይገኛል ፥ ጣዕም ሁበሉ አለ ይልቁንም ፈረስ አህልና ዐፈር ቢሰጡት ፥ የሰጡት እንደሆነ ዐፈሩን እየተወ እህሉን ይበላል ።
ወአጼንዎ ።

እጼንዎ ይገኛል ። ሐተታ አጼንዎ በሁሉ አለ ይልቁንም የሜዳ አህያ ፥ ወይቀውም ሐለስትዮ ማዕከለ አድባር ወያበቁዕ እንፎ እንዲል ፤ ከተራራ ላይ ወጥቶ አፍንጫውን ከፊት ከፊት ያደረገ እንደሆነ የማር የውኃ ጣዕም ይመጣለታል የሦስት ቀን መንገድ ገሥግሦ ሄዶ ማሩን በልቶ ውኃውን ጠጥቶ ዕለቱን ተመልሶ ከቦታው ገብቶ ያድራል ።
ወገሢሥ ።

ገሢሥ ይገኛል ፥ ገሢሥ በሁሉ አለ ይልቁንም ዝንጀሮ በትር ቈርጦ እስከ መማታት ይደርሳል ፤ የላይቤት አማርኛ በችሐበችሆ ይላል ።
ወዓዲ ተንሥአ ወነቢር ።

አፍ ቁጭ አፍ ቁጭ ማለት ይገኛል ቡኸር አታርፍም ። እንድም እናበህ ተንሥአ ነቢር መቀመጥ ያለበት መነሣት ይገኛል ። ውሻ ድመት በኋላ እግራቸው ይቀመጣሉ በፊት እግራቸው ይቆማሉ ።
እንሳሕሰሐ ።

እንሳሕሰሖ ይገኛል ። አንሳሕሰሖ በሁሉ አለ ይልቁንም ጥርኝ አታርፍም ።
ወኀድዓት ።

ኀድዓት ይገኛል ፥ ኀድዓት በሁሉ አለ ይልቁንም አንበሳ ። በሬም ያግዛል ።
ወፍትወት ።

ፍትወት ይገኛል ፤ ፍትወት በሁሉ አለ ይልቁንም ሰገኖ ፤ ሰገኖ ታበዝኀ ፍትወተ ወእምከመ ኢፀንሰት ኢትበልዕ ማዕረ እንዲል ።

ወወሊድ ።

ወሊድ ይገኛል ፤ ወሊድ በሁሉ አለ ይልቁንም ኅማ ያለሽል አታድርም ።

ወሙዓት ።

መዓት ይገኛል ፤ መዓት በሁሉ ፤ አለ ይልቁንም ግሥላ ታንቆ ይሙታባሽ ያሏት እንደሆነ ታንቃ ትሞታለችና ።

ወማህል ። ማህል ይገኛል ። ማህል በሁሉ አለ ይልቁንም ዘሆን ፤ ዘሆን ሆይ ዘሆን ሆይ ያሉት እንደሆነ መንገድ ይመራል

ወሕማም ።

ሕማም ይገኛል ። ሕማም በሁሉ አለ ይልቁንም ነብር ዓይን ሕመም ይጸናበታል ።

ወተበቅሎ ።

ተበቅሎ በሁሉ አለ ይልቁንም ግመል አጥብቆ የመታትን እስከ ስድስት እስከ ሰባት ዓመት ድረስ አትረሳውም ስፍራ ሲመቻች ገደል ገፍታ ትጥለዋለች ባጥ ብላ ትረግጠዋለች ።

ተፈሥሖ ።

ተፈሥሖ በሁሉ አለ ይልቁንም ቀበሮ ፤ ዱሮ ዘመን ቀበሮ ማዝሟ ያገኘ እንደሆነ ሲዘል በታው ይጠፋው ነበር ዛሬ ግን እጁን ጭኖ የሚይዝል ሁኗዋል የጊዜውን ከፋት መናገር ነው ።

ወኃዘን ። ኃዘን በሁሉ አለ ይልቁንም ዖፌ መንጢጥ ባሏ የሞተ እንደሆነ ወበዕፍራ ትቤጽር ልሳና ይላል ፊቷን ጸፍታ አንገቷን ሰንጥቃ ትኖራለች ፤ ሌላ መጥቶ ልድረስብሽ ያላት እንደሆነ ያን ታሳየዋለች ቢመለስ ይመለሳል የተጋፋት እንደሆነ ከወገኖቹዋ ትጠጋለች ያድኑዋታል ፤ ነዊም ። መኝታ በሁሉ አለ ይልቁንም አዞ የያዘውን ከመጣል ይደርሳል ።

ወነቂሕ ። መንቃት በሁሉ አለ ይልቁንም ቆቅ ፤ ያን ቆቅ ያሉ እንደሆነ ይህን በቅሎ ሕይወት ። ሕይወት በሁሉ አለ ይልቁንም ዖፌ ፊንክስ የሚባል ዖፍ አለ ባጅት ባጅት መቶ ዘመን ይታደሳልና ። ይህስ የታወቀ ነው ብሎ እንደ ፍገራ እሞራ ጥርቁ የተላለፈ እንደሆነ ጭሮ መብላቷ አይሆንለትም ከዕንጨት ከድንጋይም የመታው እንደሆነ ይተካከልለታል ጭሮ ይበላል ። ወመዊት ። ሞት በሁሉ አለ ይልቁንም አይጥና ድንቢጥ ጭላት የበልጉ ለመኸር የመኸሩ ለበልግ አይገኙም ።

ወኵሎ ሰለ ዝንቱ በከመ ይትረከብ ዝብሙስተ እንስሳ ነሳሱለትና ይህን የምስስ ሁሉ በእንስሳት ባሕርይ እንዳለ በሰውም በእንስሳ ባሕርዩ ይህ ሁሉ አለ ወዓዲ አከበሮ በንፍሐት ዘይእቲ ማኅተመ ሕይወት መንፈሳዊት እንተ ባቲ አከበሮ እምኵሉ ፍጥረት ዘታሕተ ሰማይ ።

ከአራቱ ባሕርያት አዋሕዶ ፈጠረው ብሎ ነበርና ዳግመኛ ባራቱ ማዕዘን ካለ ፍጥረት ለይቶ ባከበረበት የሥጋ ሕይወት የደመ ነፍስ ሕይወት በምትሆን በነባቢት ነፍስ አከበረው ።

ወትትዓወቅ በኃይለ ንባብ ፤
ምሥጢር በመናገር ትታወቃለች ።

ዛይእቲ አርአያ ገጹ ለእግዚአብሔር ወአምሳሊሁ ይቺውም የእግዚአብሔር መታወቂያው ናት ምሳሌውም ናት ።
በከመ ይቤ መጽሐፍ ፤

መጽሐፍ ንግበር ሰብአ በአርዓያነ ወበአምሳሊነ እንዳለ ።

ወይእቲ ዘኢትትለከፍ ፤
የማትያዝ የማትዳሰስ ናት ፤
ወዘኢግብርት ። ግብር እምግብር ያልተፈጠረች ናት ። አንድም አጥብቅ ፤ ያፃገብሯት ናት ።
ሀላዊት ፤ ነዋሪት ናት

ወዘኢመዋቲት ፤ የማትሞት ናት ፤
ኩናኒተ ሥጋ ወኃይሉ ፤
ሥጋን ደመ ነፍስን የምትገዛ ናት አንድም ሥጋን የምትገዛ ናት ወኃይሉ ጠበቃው ናት
በእንተ ዘኮነት አሐተ ውስተ ኵሉ ፤
በፈቃድ አንድ ስለሆነች ።

ወባቲ ይትረከብ ጥበብ ዘየሐለብ ልብ ወየኃሪ ፤ ልብ የሚሻው ጥበብ በሷ ይገኛል ።
ወአእምሮ አዝማናት ።

ፀሐይ መጸው ክረምት ፀጋይ ማወቅ በሷ ይገኛል ይህንስ እንስሳትም ያውቁታል ብሎ ዓዝማኒ መንግሥተ ሰማያትን ማወቅ ይገኛል ።

ወመካናት ። ቆላ ደጋን ማወቅ በሷ ይገኛል ፤ ይህንስ እንስሳትም ያውቁታል ብሎ ቆላ ገሃነም ደጋ መንግሥተ ሰማያት ማወቅን በሷ ይገኛል ወኩላ ምግባራት እንተ ትከውን በዘይእቲ ሳዕሌሁ የሚሠራው ሥራ ሁሉ እሱን ተዋሕዳ ባለች በሷ ነው ፤ አንድም እሷን ተዋሕዶ ሳለ በሥጋ የሚሠራ ሥራ ሁሉ ባቲ ይትረከብ ።

በሥልጣን ባሕታዊት ። በዕውቀት ልዩ ናት
ሥዕልት ዘእንበለ ገቢር ።
ግብር እምግብር ሳይሆን የተፈጠረች ናት ።

ወገብረ ላቲ ሥልጣነ በውስቴታ ትግበር በከመ ኅርየት እንዘ አልቦ ዘይኬንና ወዘይጌይላ ።

የሚገዛት የሚያዛት ሳይኖር የወደደችውን እንደወደደች ታደርግ ዘንድ አእምሮ ጠባይዕን ሳለባት ።
ከመ ይኩን ሠናያቲሃ ወአከያቲሃ በሥምረተ ሕሊናሃ ።

ፀጎነቷም ክፋቷም በፈቃደ ይሆን ዘንድ ።
በአምሳለ መላእክት ።

ሠናያቲሃ በአምሳለ መላእክት ፡ በሚካኤል በገብር ኤል አምሳል ።

እከያቲሃ በአምሳለ መላእክት ብለሀ ግጠም ።
በኢጋንንት አምሳል ይሆን ዘንድ ።
ወተፈጸመ ፍጥረቱ ለአዳም በዝንቱ ግብር ።

የአዳም ተፈጥሮ በዚህ ተፈጸመ ።
ዘቦ ውስቴቱ ፫ቱ ኃይል ።
ሦስት ግብር ሦስት ባሕርይ ባለው ።

ኃይለ ዘርእ ። የዘር ግብር የዘር ባሕርይ ባለው ።
ወኃይለ እንስሳ ።

የደመ ነፍስ ግብር የደመ ባሕርይ ባለው ።
ወኃይለ ንባብ ።
የነባቢት ነፍስ ግብር ባለው ። ይቀየን

ሦስተኛ ጉባኤ ።

ወአልበሶ አልባሰ ብሩሃ ።

ከአራቱ ባሕርያት ፈጥሮ ከእንስሳት ከአራዊት ለይቶ በነባቢት ነፍስ አከበረው ብሎ ነበርና ልጅነትን ስጠው ፤ እስመ አልበስከኒ ልብሰ ትፍሥሕት ወልብሰ መድኃኒት እንዲል ።

አካሉን ሲያይ ብሩህ አለ ፡ ህብሩን ሲያይ አልባስ ብሎ አበዛ ፡ ከዚህ ዕለቱን አስመስሎታል አክሲማሮስ በ፮ ቀን ብሎ ለይቶ ተናግሯል ።

ወገብረ ሎቱ ሥልጣነ ለርእሱ ።
ሥራ ሠርቶ ሊጠቀምበት መንፈሳዊ ዕውቀትን ሰጠው ።
ወአንጥዮ ሞተ ።
በዓቂበ ሕግ እንዳይሞት አደረገው ።
ወረሰዮ ሥሉጠ ላእለ ኵሉ ፍጥረት ዘታሕተ ሰማይ በአራቱ ማዕዘን ያሉትን ፍጥረት አሰገዛው ፡ ወአወልጠና ፡ አራቱ ማዕዘን ባሉ ፍጥረት አሠለጠነው ወፈጠረ ሎቱ እምሥጋሁ ረድኤተ ።
ከአካሉ ልትረዳው ፈጠረለት ፡ በአቅሉ ክበደ ዋዕይ ልጅ በማስገኘት አንድም እሱ የአፍአውን እሷ የውስጡን በማከናወን ።
ወሰመያሔዋን ።
ሴቷን ሔዋን አላት ፤ ሕይወት ማለት ነው እንደግብሩስ ሞት በተባለች በተገባት ነበር ሕያዋን ጻድቃን ከሷ የሚወለዱ ስለሆነ ሕይወት አላት ።
ወአንበሮሙ ውስተ ገነተ ዔዶም ጽባሐዊ ።

መወደድ ባለው በምሥራቅ በኩል በገነት አኖራቸው አንድም ፤ ጽባሐዊ መወደድ ባለው በገነት ምሥራቅ አኖራቸው አራት ማዕዘን አለውና ።

ወወሀቦሙ ይትፈሥሑ በኵሉ ሠናያት አምላካውያት ዘእንበለ ክልዓት ።

ወሀቦሙ ዘእንበለ ክልዓት ፡ ከአምላክ በሚገኘው ነገር ሁሉ ደስ ይላቸው ዘንድ ያለመከልከል ሰጣቸው ይትፈሥሑ ዘእንበለ ክልዒትያለመከልከል ደስ ይላቸው ዘንድ ።

ወወሰነ ሎሙ ትእዛዘ በእንተ አሐቲ ዕፅ ባሕቲታ ፡ ስለ አንዲት ዕፅ ብቻ ትእዛዝ ወሰነባቸው ።
ወይእቲ ዕፅ እንተ ታሌቡ ሠናየ ወእኩየ ።
ያቺም ዕፅ ባይበሏት በጐ ቢበሏት ክፉ የምታስታውቅ ናት ።

ከመ ኢይብልዑ እምኔሃ ።
ወሰነ ከመ ኢይብል እምኔሃ ከሷ እንዳይበሉ ትእዛዝ ወሰነባቸው ።

ሐተታ ፤ የገዥና የተገዥ ምልክት የዓቂበ ሕግ ምልክት ጾምንም በዚህ ነገረው ።
እስመ አመ ይበልዑ እምኔሃ ሞተ ይመውቱ ።
ከሷ የበሉ እንደሆነ የሞት ሞት ይሞታሉና ብሎ ወለእመ ሰምዑ እንከ ትእዛዞ ይከውኖሙ ሕይወተ ዘለዓለም ።

ትእዛዙን ቢጠብቁ የዘለዓለም ድኅነት ይሆናችዋል ብሎ ።
አንድም ትእዛዙን ጠብቀው ቢሆን የዘለዓለም ድኅነት በሆናቸው ነበር ።
ወለእመሰ ተዓደው ይከውኖሙ ሞተ ።
ትእዛዙን ግን ቢያፈርሱ ሞት ተፈረደባቸው ።
ወሶበ ርእየ ሰይጣን ዕበየ ስብሐቲሁ ወክብራቲሁ ሰይጣን የራሱን ደግ ክብሩን ፡ ደግ ጌትነቱን ባየ ጊዜ ወብርሃነ ዘይትዓፀፍ ቦቱ ።

ተሰጥቶት የነበረውን ጸጋውን ባየ ጊዜ ።
ወርእየ ርእሶ በርእሱ እምድኅረ ክብር ወሢመት ዓባይ ።

ከሹመቱ ከተሻረ ከልዕልናው ከተዋረደ በኋላ ራሱን በራሱ በመረመረ ጊዜ ወድቀ አንድም መልስ የአዳም ደግ ክብሩን ደግ ጌትነቱን ባየ ጊዜ ለአዳም የተሰጠውን ጸጋውን ባየ ጊዜ አዳም ከተሾመ ከከበረ በኋላ የራሱን ክብር በአዳም ላይ ሁኖ ባየ ጊዜ ወድቀ በድቀተ ቅንዓት ።

ቅንዓት ባመጣው ድቀት ወደቀ ደንገፀ በድንጋፄ ቅንዓት ፡ ቅንዓት ባመጣው ድንጋፄ ደነገፀ ፡ ኃዘን ባዘን

ቅንዓት ተከዘ በትካዘ ቅንዓት ፡ ኃዘን ትካዝ ባመጣው ቅንዓት አዘነ ፤ ወድቀ መውዱቀ ውዱቅ ይላል ፤ መውዱቅ ዲያብሎስ ውዱቅ አዳም ነው አዳምን ያሳተ ዲያብሎስ ወደቀ ድል ሆነ ።

ወቀብጸ ተስፋሁ ። ተስፋ ቆረጸ
በእንተ ዘኢፈቀዶቱ እግዚአብሔር ኪያሁ ፤
እግዚአብሔር እሱን ባለመሻቱ ፤
ወኢያግብአ ውስተ ዘቀዳሚ መንበሩ ፤
ወደተደመ ቦታው ወደቀደመ ማዕርጉ ባለመመለሱ
ወኢተርፈ ሎቱ እምነ ዘይእኅዝ ዘእንበለ ዘያስግዶ ለብእሲ ከመ ያውፅእ እምፈቃደ ፈጣሪሁ ።

ወይም እንጂ ይመልሰኝ ይሆናል ብሎ ነበርና አዳምን ከፈጣሪው ትእዛዝ ያወጣው ዘንድ አዳምን ከሚያስትበት ግብር በቀር ከያዘው ከረዘዘው የቀረለት የለም ።
ወነሥአ ሎቱ ተኃይሎተ ዘበእኪት ፤

የበጐ መበረታታትአለና የከፋ መበራታታትን አደረገ
ወመንሱት ወልታ
ወልታ መንሱት ሲል ነው አዳምን ድል የሚነሳበትን ጋሻ አነገበ ።

ወመጽአ መንገለ ብእሲ በውእቱ ተኃይሎት ጸዋግ
በከፋ መበራታት ወደአዳም መጣ ፤ ሐተታ ፤ አሣግዮስ አውግብዮስ በገነት እንዳሉ ሁነው ይጽፋሉ ወአምጽእዎ ለውእቱ ንዋይ እምኢየሩሳሌም እንዳለ ነቢይ በኢየሩሳሌም ሳለ ፀባቤን እንዳለ አድርጎ ፤ በእንተ ምክንያት ዘያወፅእ ቦቱ እምገድል ሥናይት ከበጐ ግብር ስለሚያወጣበት ምክንያት እምገነት ሥናይት እምፍናት ሥናይት እምግእዝ ሥናይት እምዕረፍት ሥናይት ይላል ።
ወጸንሃ እንከ ።

ሸመቀበት ሰው በጠላቱ እንዲሸምቅ ጦሩን ሰንግሎ ጋሻውን ወልውሎ ፤ አንድም ድል የሚነሣበትን ግብር ዐወቀ ፤ አንድም የሚለያዩበትን ጊዜ ጠበቀ ። በከመ የአምሮን ጸላዒ ለጊዜያት ለነኒ ይደልወነ ከመ ናአምር ድካሞቲነ እንዲል ።
ወናሁ ውእቱ ምስለ ረድኤቱ ተሠልጡ ውስተ ኵሉ ዕፀወ ገነት ።

ተሠልጡ ካለ ውእቱ ወረድኤቱ ምስለ ረድኤቱም ካለ ተሠልጠ ቢል በቀና ነበር ልማደ መጽሐፍ ነው ሌሊት ምስለ መዓልት ይትካፈልዎ ለዘመን በዕሪና ።
ከንቶ ይትናገሩ ፩ዱ ምስለ ካልኡ እንዲል ፤ እሷ እሱ በገነት ባለው ዕፅ ሁሉ ሠልጥነው ነበር ።
ዘእንበለ እሐቲ ዕፅ ባሕቲታ እንተ ከልአ እምኔሃ ፤
እሷን አትብላ ብሎ ከከለከለው ካንዲት ዕፅ በቀር
ወተፈሥሐ እንከ ዓቢየ ፍሥሐ ።
ፈጽሞ ደስ አለው ።

ወአእመረ ከመ በውእቱ ዕፅ ይመውኦ ።
በዕፀ በለስ ድል እንዲነሣው ዐወቀልና ።
ወያወፅኦሙ ለአዳም ወለሔዋን እምፍግዓሆሙ ።
አዳምና ሔዋንን ከተድላቸው ከደስታቸው እንዲለያቸው ፤ አንድም ተድላ ደስታ ከሚያደርጉባት ከገነት እንዲያወጣቸው ዐወቀልና ፤
ወተኀብአ እንከ ውስተ ሥጋ ከይሲ ።
በሥጋ ከይሲ ተሰወረ ።
ወረሰያ ምክንያተ ለኃጉል ።
ለጉዳት ምክንያት አደረጋት ፤ ታሪክ እንስሳት አራዊት ከአዳም ዘንድ ሄዱ ስለምን ቢሉ ስም ለመሰየም ስምስ ተሰይመዋል እስከዚያ ወዴት ኑረው ብሎ ለደጅ ጥናት ሄደው አርደህ ብባን አሉት ። ምን አገኙ በገነት ባለ ዕፅ ሁሉ አሠልጥኖናል ፤ እናንተስ ባላችሁበት ያርባችሁ ያብዛችሁ ያስፋፋችሁ ብሎ መርቆ ሰደዳቸው ፤ ዲያብሎስ ከመንገድ ቆይቶ ወዴት ሄዳችሁ ኑራችኋል አላቸው ። ከአዳም ከጌታችን አሉት አዳም ጌታችሁ ምን ይመስላል አላቸው ከፀሐይ ሰባት እጅ ያበራል አሉት በዚያውስ ላይ ይህን ያህል ደስታ ምን ተገኝቷል አላቸው ። እንዲህ ብገን ሰው እንዲህ አለን ሞት ቢቀርልን አሉት ። ያችን ዕፅ ቆርጦ ማን ካፉ ባገባልኝ ነበር ብሏል ። በሌላው ቀን ሲሄዱ አገኛቸው ወዴት ትሄዳላችሁ አላቸው ከአዳም ከጌታችን አሉት ። አስከተሉኝ አላቸው ። አዳም ጌታችን መልክ መልካም ነው አንተ መልክ ጥፉ ብለው ትተውት ሄዱ ። አብርል አዝርል የሚባሉ የገነት አዕዋፍ መጡ አስከትሉኝ አላቸው አዳም ጌታችን መልካም አንተ ክፉ ብለው ጥለውት ሄዱ ። እባብ መጣች የገመል ወሳብሬ ታህል ነበር ወዴት ትሄጃለሽ አላት ወደ አዳም ወደ ጌታዬ አለችው ፤ አስከትይኝ አላት አዳም ጌታዬ መልካም ነው አንተ ክፉ ነህ አይሆንም አለችው ። ክፉ ከሌለ መልካም በምን ይታወቃል መስሎሻል ። በዚያውስ ላይ ባንቺ እንጂ አምር የለም ብሎ በውዳሴ ከንቱ ጠለፋት ፤ አስከትላው ሄደች ቁልቁለቱን ጨርሰው አዳገቱ ደረሱ ፤ የቆላ መንገድ እንጂ ካልተዋወቁበት አይሆንም እየተዛዘልን እንውጣው አላት እሽ አትሰው ነይ ልዘልሽ አላት ጥቂት እልፍ አድርጎ በጽሐ በፏ ሥግው ሆነ ፤ ከአዳም ዘንድ ሄደ ጸሎት ይዞ አገኘው አስቀድሞ በዚህ ድል ነሣው በሐኬ ንጉሥ ሰማያት ወምድር አለው ፍልጥ አርጌ ምድር ፤ ንጉሥ ምድር ነኝ እንጂ ንጉሥ ሰማያት ፈጣሪዬ ነው አለው ። ሔዋን ወዴት ናት አለው ፤ ከዚያ አለች አለው ቢሄድ ሥራ ፈትታ አገኛት በዚህ ድል ነሣት ።
ወአስተርአያ ለሔዋን በነገር ጥዑም ዘምሉእ ጉሕሉት ከዳት ተንኮልን በተመላ ደስ በሚያሰኝ አነጋገር ሔዋንን ተናገራት ፡ በሐኪ ንግሥተ ሰማይ ወምድር አላት ደስፈቅ አላት ፤

ወይቤላ በእንተ ምንት ይቤለክሙ እግዚአብሔር ኢትብልዑ እምዅሉ ዕፀው ዘውስተ ገነት ።

ለይቼ የጠየቅኋት እንደሆነ ታውቅብኛለች ብሎ በገነት ካለው ዛፍ ሁሉ አትብሉ ያላችሁ ስለምንነው አላት ፤
ወትቤሎ ንበልዕሰ እምዅሉ ዕፀው ዘውስተ ገነት

በገነትስ ካለ ዕፅ ሁሉ እንበላለን ፤
ወባሕቱ ፍሬ ዕፀሰ ዘውስተ ገነት ይቤለነ እግዚአብሔር ኢትብልዑ እምኔሃ ። ነገር ግን በገነት እንዲት ዕፅ አለች እሷን አትብሉ ብሎናል ።
ከመ ኢትሙቱ ሞተ ፤

ያው ቅሉ ነፍሳን አይደለም የሞት ሞት ትሞታላችሁ ብሎ ነው እንጂ አለችው ፤
ወይቤላ አኮ ሞተ ዘትመውቱ ።

ጣዖቱን ይሰብካል የሞት ሞት ትሞታላችሁ ብሎ አይደለም ፤
ወባሕቱ የአምር እግዚአብሔር ከመ ሶበ በላዕክሙ እምኔሃ ይትከሠታ አዕይንቲክሙ ወትከውኑ ከመ እምላክ ።

በበላችሁ ጊዜ የእምላክነት ዕውቀት እንድታውቁ እንደ እምላክ እንድትሆኑ ያውቃልና ፤
ወትአምሩ ከመ ሠናየ ወእኩየ ።

የሰውነት የእምላክነት ዕውቀት እንድታውቁ ያውቃልና ስለዚህ ነው እንጂ የሞት ሞት ትሞታላችሁ ብሎ አይደለም ።
ወእፍተዊ ከመ ትብላዕ እምውእቱ ዕፅ ፤
ዕፀ በለስን ትበላ ዘንድ አስወደዳት ልብላ ልብላ አሰኛት ።
ወታብልዖ ለአዳም ፤
ለአዳም ታበላው ዘንድ ፤
ከመ ይኩኑ ዘየአምሩ ሠናየ ወእኩየ ።

የሰውነትን የእምላክነትን ዕውቀት ያውቁ ዘንድ ፤
ወሶበ ጸነቶ ኅበ ነገሩ ጸንዓ ላዕሌሃ ፍትወተ ጥዕመት ምሰለ ሕሊና ትዕቢት ፤
ነገሩን በተቀበለችው ጊዜ እምላክ እሆናለሁ በማለት ልብላ ልብላ የማለት ፈቃድ አደረባት ። ልብላ አሰኛት ፤

ወአፍጠነት ወበዓልት እምይእቲ ዕፅ ፤
ፈጥና ቆርጳ በላች ።
ወአብልዓቶ ለአዳም ፤
ለአዳምም አበላችው ። ሐተታ ነገሩን እንደ ተቀበለችው አውቆ የእምላክነት ነገር እንዲህ አይደለም የተቀዳደማችሁ እንደሆነ ያንድኛችሁ ይቀርባችኋል ለርሱ በቀኝ እጅሽ ላንቺ በግራ እጅሽ ቆርጠሽ አንድ ጊዜ ጉረሷት አላት ። የሷ ሲነግት አይቶ እሱ ያመልጠኛል የሱ ሲነግው አይታ እሷ ታመልጠኛለች ብሎ ፤ ዛሬም ሴቶች ይህ አብነት ሁኗቸው ብቀኝ እጃቸው ለባሎቻቸው እያጎረሱ በግራ እጃቸው ይበላሉ ።
ወወጽአ እምትእዛዘ እግዚአሙ ወተዓደው እምነገሩ ፤
ከፈጣሪያቸው ትእዛዝ ወጡ ፤
ወኮኑ ቀታልያነ ርእሶሙ ፤
ራሳቸውን አጥፊ ሆኑ ።
ወተሰዱ እምድረ ገነት ኀበ ምድረ ሕማም ፤

ከገነት ወደ ምድረ ፋይድ ወረዱ ፤ ሐተታ ምድረ ፋይድ ማለት ምድረ ኃጣር ወመርገም ምድረ ድንጋጼ ወረዓድ ማለት ነው ።
ወእርአያ ኀሱም ወኅሱር ፤
ከፋና መልካም ቀይና ጥቁር አጭርና ረጅም ቀጭንና ወፍራም ወደሚፈጠርበት ።
ወሲሳየ ኃዘን ።

ቢያገኙት ቋንጣን ቢያጡት ቀጠና ወደሚሆንበት ወፈትሐ ላዕሌሆሙ በሞት እስከ ለዝሉፉ ፤

እምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን እስኪፈጸም በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስን ፤ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነምን ፈረደባቸው ።
ወእምድኅረ ተዓርቁ እምልብሰ ብርሃን ዘቲአጽፉ ቦቱ ።

ከተሰጣቸው ከጸጋቸው ከተለዩ በኋላ ፡ አንድም የተሰጣቸው ጸጋቸውን ባጡ ጊዜ ።
ተኃፍረ አዳም እምእግዚአብሔር ፤
ከእግዚአብሔር የተነሳ አዳም ፈራ ፤ ሐተታ ሰኩና ብእሲ እያሰማ ቢመጣ አዳም ፈርቶ ከእንጨት ውስጥ ተሰውሮ ተገኝቷል ።
በእንተ ተዓድዎቱ ።
ከትእዛዙ ስለወጸ ፈራ ።
ወናሁ ቀደመ ቃል ከመ ነፍስ ነባቢት እንዘ አልቦ ዘይኴንና ወዘይጌይላ ፤
ተኃፍረ ብሎ ነበርና በምን አውቆ ትሉኝ እንደ ሆነ ። የሚገዛት የሚያዛት ሳይኖር ነፍስ አዋቂት እንደሆነች አስቀድሞ ተነግሯል ወንብረ ላቲ ሥልጣነ በውስቴታ ከመ ትግበር ዘከመ ኃረየት ተብሎ ወለእመሰ ነበረት በትእዛዙ እምኮነት ብርሀተ በብርሃነ ትእዛዙ ፤
ትእዛዙን ጠብቃ ኑራ ቢሆን ትእዛዙን ቢጠብቁ በሚገኝ ብርሃን ትእዛዙን በመጠበቅ ብርሃን ብርሀት በሆነች ነበር ።
ወሶበ ጸነት እንከ ኀበ ተዓድዎተ ነገሩ ጸልመት በጽልመተ ተአድዎ ።
ትእዛዙን ግን ቢያፈርሱ ፤ ትእዛዙን ቢያፈርሱ በሚመጣ ጨለማ ። ትእዛዙን በማፍረስ ጭልማነት ጨለመች ማለት ። ትእዛዙን ቢያፈርሱ በሚመጣ ድንቁርና ደነቁረች ።

እስመ አልቦ ዘይኄንና ወዘይኄይሳ በውስተ ፈቃደ ኅዕሴሃ ፤
በፈቓዱ የሚያዛት የሚገዛት የለምና ፤ እመ ነበረት ለበጎው ፤ የሚያዛት የሚገዛት ሳይኖር ሶበ ጸነት ለክፋው ፤
ወበእንተ ዝንቱ ይረክቦ ለብእሲ ኀንት ፤
ኀንተ ሲል ነው ፤ መገናኘት የጋራ ከሆነ ብሎ እን ዲህ አለ እንጂ ። በስዚህ አዳም ኀንትን ይወርሳል ። [illegible] እምእኩይ ውስተ ሠናይ ወገቢሮቱ ። ክፋ ወደ በጎ ቢመለስ በጐውን ወደ ማድረግ ቢመ ለስ፤ ኀንትን ይወርሳል ፤

ወሶበ ጸነ እምሠናይ ኀበ እኩይ ወገቢሮቱ ፣ ከበጎ ወደክፋ ቢመለስ ክፋውን ቢያደርግ ፤
ደለዎ ሆነኔ ፤
ሞት ተፈረደበት ።
ወበጸኒኖቱ ለአዳም ኀበ ፈቃደ ሰይጣን ወተዓድ ዎተ ፈጣሪሁ ኮነ እንከ ገብሮ ለሰይጣን ፤
አዳም የሰይጣንን ነገር በመቀበሉ ከፈጣሪው ትእዛዝ በመውጣቱ የሰይጣን ተገዢ ሆነ ።
ወታሕተ ሥልጣኑ ፤
ከሥልጣኑ በታች ሆነ ፤

ወተርፈ ውስተ ምድር ኀዙነ ወትኩዘ ፤ በዚህ ዓለም ያዘነ የተከዘ ሁኖ ኖረ ፣ አንድም ኮነ ገብሮ ለሰይጣን ታሕተ ሥልጣኑ፤ከሥልጣኑ በታች ሁኖ የሰይጣን ተገዢ ሆነ ። ወተርፈ ፤ በዚህም ዓለም ያዘነ የተከዘ ሁኖ ኖረ ፤
በእንተ ዘገብረ ተዓድዎተ ፤ ከፈጣሪው ትእዛዝ ስለወጣ ።
ወዓለወ ትእዛዘ ፈጣሪሁ ፤
የፈጣሪውን ትእዛዝ ስላፈረሰ ፤
ወእምንዳቤ እንተ ረከቦ ፤
ካገኘው ጸዋትወ መከራ የተነሣ ፤
እምኃዘን ወእምአውያት ፤
ከኃዘን ከልቅሶ የተነሣ ፤
ወከኢወ አንብዕ ውዑይ ።

ቁጡ እንባን ከማፍሰስ የተነሣ ። ሐተታ ቁጡ እንባ ዓይን ከማጥፋት ያደርሳል ። አንድም ውዑይ እንባ ከማፍሰስ የተነሣ ።
ረስዓ ኀንተ እንተ ነበረ ባቲ ፤
የነበረባትን ኀንትን ዘነጋ ።
ወእልቦቱ ካልዕ ሕሊና ዘእንበለ ብካይ ላዕለ ኃጢ አቱ ፤

በኃጢአቱ ከማዘን ከማልቀስ በቀር ማዘን ማልቀስ ነው እንጂ ሌላ ግዳጅ አልነበረውም ፤ ሐተታ አዳ ምን የቤተ ፈት ልማድ አላገኘውም ቤተ ፈት በዚህ ጊዜ እበላ እጠጣ እለብስ አጌጥ የነበረ ቀረ ብኝ ብሎ ያዝናል ፣ እሱ ግን የማይገባ ሥራ ሠርቼ ፈጣሪዬን አሳዘንሁት ብሎ ነው እንጂ በገነት ሳለሁ አደርገው የነበረው ተድላ ደስታ ቀረብኝ ብሎ አይደለምና በኃጢአቱ ከማዘን ከማልቀስ በቀር በኃጢአቱ ማዘን ማልቀስ ነው እንጂ ግዳጅ አል ነበረውም አለ ፤
ወእአመረ እግዚአብሔር ይትለዓል ዝክሩ ንስሐሁ ወገዓሮ ብዙኃ ወምንዳቤ እንተ ረከቦ ተሣሃለ ላዕ ሌሁ ወምሕሮ ።
በልብ መታሰቡ በቃል መነገሩ ከፍ ከፍ ይበልና አላበጀሁም ማለቱን ብዙ መጨነቁን ጸዋትወ መከ ራውን አይቶ ይቅር አለው አዘነለት ፤
ወፈቀደ ያድኅኖ እምዳኅጹ በእንተ ፪ ገጸት ።
ስለ ሁለት ነገር ከፍዳው ሊያድነው ወደደ ፣
፩ዱ በእንተ ንስሐሁ ፤
ከሁለቱ አንዱ አላበጀሁም በማለቱ ነው ፣
ወገዓረ ብካዩ ለኃሚሠ ሥርየት ፤
ኃጢአቱ ሊሠረይለት ኃጢአቱን ሊያሥተሰርይለት እያለቀሰ በመጨነቁ ነው ።

ወረሲአቱ ኀንተ ወፍግዓሁ ወተድላሁ ፤
ኀንትን በመዘንጋቱ ተድላው ደስታውን በመዘን ጋቱ ነው ።

ወካልዕስ በእንተ ዘተሕተ ውእቱ ተትሕቶተ ወካልዕሂ ሲል ነው ሁለተኛውም እሱ ፈጽሞ ስለ ተዋረደ ነው ።
ወዓዲ አጥረየ ሰይጣን መዊዓ ወኃይለ ላዕለ አዳም ወቀንዮ ፤
ዳግመኛ ሰይጣን በአዳም ላይ ኃይልን መዊዕን ገን ዘብ አደረገ ።
ወኮነ ጼዋሁ ፤ ምርኮው ሆነ

ወኮሉ ዘርዑ ምስሌሁ ፤
ልጆቹም ከሱ ጋራ እንደሱ ተገዙ ።
ወተሰልጠ ሰይጣን ዲቤሆሙ ለእስግዶ በብዙኀ ግብ ራት ። አሳታቸው ብሎ ነበርና ዳግመኛ በብዙ ነገር ለማሳት ሰይጣን ሠለጠነባቸው ።
ወመንከራት ትልዎት ፤
ቀጽሎ ቀጽሎ በሚደረግ በምትሐት ተአምራት ፤ አንድም ወመንከራት ትልዎተ ይባል ። ቀጽሎ ቀጽሎ እራድፎ እራድፎ በሚመጣ መከራ ሠለጠነባቸው ወቦ እምኔሆሙ ዘመሐረ ከመ ፍጥረት ተፈጥረት እምኀበ ርእሳ ባሕቲታ ዘእንበለ ሠራዒ ወገባሪ ። ከርሳቸው ወገን ፍጥረት ያለ ሠራዒ ያለ መጋቢ ከባሕርይዋ እንደ ተፈጠረች ያስተማረ አለ እን ማኒ ወቦ እምኔሆሙ ዘመሐረ ከመ ፀሐይ ወወርሀ ወከ ዋክብት አሙንቱ እለ ፈጠሩ ዓለመ ፤

ሰማይ ምድርን የፈጠሩ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት እንደሆኑ ያስተማራቸው አሉ ። ጸርዓውያን ፀሐይ ጨረቃን ሰባቱን ከዋክብት ያመልኩ ነበር ።

ወቦ ዘመሐረ ከመ አምልኮ አራዊት ወእንስሳ ይእቲ ፍኖት በእማን ጥይቅት ፤

አምልኮተ አራዊት አምልኮተ እንስሳ በውነት የተረዳት ሃይማኖት እንደሆነች ያስተማራቸው አሉ ።
ወባቲ ይትረከባ ፈቃዳት ።
የሚሹት ነገር በሷ እንዲገኝ ።
ወይትፈጸማ ባቲ ስእለታት ።

ልመናም በሷ እንዲገኝ ያስተማራቸው አሉ ። ሐተታ ግብጻውያን ላም ያመልኩ ነበር ባቢሎናውያንም ዘንዶ ያመልኩ ነበር ፣

ወአርስእሙ እግዚአብሔርሃ አምላኮሙ ።
ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን አስካዷቸው ።

ወቦኡ ውስተ ልጎተ ርስአት ፤ ወደ ፍጹም ዝንጋኤ ገቡ ፤

ወተመንኖት ወተቀንዮት ለብዙኅ ኃጢአት ዘዘዚአሁ ልዩ ልዩ የሚሆን ለብዙ ኃጢአትም ወደ መገዛት ወደ መናቅ ገቡ ።

አምቅትለት ፤ ነፍስ ከመግደል ወገን
ወእምዝሙት ወሐሰት ወሐሜት ።
ከዝሙት ከሐሰት ከሐሜት ወገን አንዱ ብቻ ሠርቶት አይቀርምና በከፊል ተናገረው ።
ወአዎኦት ።
ሰውን እግዚአብሔርን ከመበደል ወገን ፤
ወትዕግልት ። ከቅሚያ ወገን
ወአምልኮተ ጣዖት ዘግብረ እድ ፤
የሰው እጅ ሥራ የሚሆን ጣዖትን ከማምለክ ወገን
ወክሂደ እግዚአብሔር ፤
እግዚአብሔርን ከመካድ ወገን ።
ወዘይመስሎ ለዝንቱ ።

ነማማሰትና ይህን ከመሰለ ወገን ለብዙ ኃጢአት ወደ መገዛት ገቡ ።
ወኮኑ ሰይጣናት ውኩላን ፤
ሰይጣናት ቁራኞች ሆኑ ።
ወሥሉጣነ በአዳም ወበኵሉ ዘርዑ ውስተ አሕጉሉ በአዳም በልጆቹም ሁሉ በቁራኝነት የሠለጠኑ ሆኑ ከመ ጺውዋን ፤

ምርኮኞች እንደመሆናቸው ፣ እንድም ማራኪ በምርኮኞቹ እንዲሠለጥን ።

ወሰዘሞተ እምኔሆሙ የአሥሩ ነፍሶ ውስተ ሲኦል ይህም ሊታወቅ ከሳቸው ወገን የሞተውን ሥጋውን በመቃብር ነፍሱን በሲኦል በገሃነም ተቁራኝተው ይኖሩ ነበር ። አሜሃ ይትፈነዋ ነፍሳት ውስተ ገሃነም እስከ ይመልአ አብያተ ሞት እንዲል ።

ወኮነ ቦሙ ዝንቱ ግብር ለዝሉፉ እስከ ተፍጻሜተ ፶፻ ወ፭፻ ዓመት እምፍጥረቱ ለአዳም ፤ አዳም ከተፈጠረ ጀምሮ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ቁራኝነት ፈጽሞ ተደረገባቸው ።

አራተኛ ጉባኤ ።

ወፈቀደ እግዚአብሔር አድኅኖተ ዓለም በሣህሉ ወበምሕረቱ ።
በይቅርታው በቸርነቱ ብዛት እግዚአብሔር ዓለምን ማዳን ወዶ ፤
ወርእየ ተግባረ እደዊሁ እለ እምጽአሙ እምተኃጥኦ ኀበ ተረክቦ ፤

ካለመኖር ወደ መኖር እምኀበ እልቦ ኀበ ቦ ከኢምንት ወደምንት አምጥቶ የፈጠራቸውን ፍጥረቶቹን አይቶ ። አንድም አምኃጢዕ ኀበ ረኪብ ይላል አብነት ካጣ በኋላ ያገኛቸውን ፍጥረቶቹን አይቶ ፣ ወአክበሮሙ ላዕለ ኵሉ ፍጥረት ዘታሕተ ሰማይ ከሰማይ በታች ባሉ ፍጥረታት ሁሉ እንዲሠለጠናቸው አይቶ ።
ከመ በዝኃት ወፈድፈደት ኀበ ተጼውዎተ ሰይጣን ወደሰይጣን ምርኮኝነት መሄዳቸው ፈጽማ እንደጸናት ዐውቆ ።
ወቀንየቱ መሪር ፤
ወደጽኑ እገዛቱ መሄዳቸው እንደጸናች ዐውቆ ።
ምሕሮሙ በዕበየ ሣህሉ ወምሕረቱ ወኂሩተ ሠናይቱ ፤
በይቅርታው በቸርነቱ ብዛት አዘነላቸው ።
ወፈትሖሙ እመዋቅሕቲሁ ፤
ከቁራኝነቱ አዳናቸው ።
ወእምጼዋዌሁ ማኅጐሊ ፤

ጥፋት ካለበት ምርኮኝነቱ ፣ ወእምጼዋዌ ማኃጉሊ ይላል ። ሰይጣንን በግብሩ ማኃጉሊ አለው ከሰይጣን ምርኮኝነት ፈትሖሙ አዳናቸው ።
በዘይሜኒ ጽድቀ ወርትዐ ።

ባማረ በተወደደ ፍርዱ አዳናቸው ። ወበድልወት ኮነ ኵነኔ እግዚአብሔር ወአድኃነነ በፍትሐ ጽድቅ ወርትዕ እንዲል ። ጌታ የገደልክ ገደልክ የበደልክ በደልክ በቃህ አላለምና በካሳ ብሏል እንጅ ፤
ወኢኃደጎሙ ውስተ ኃጉል ለዝሉፉ በዕደ ሰይጣን ።
በሰይጣን እጅ እንደተያዙ ሊቀሩ በቁራኝነት ፈጽሞ አልተዋቸውም ።
ወኢሞአ በኃይሉ መዋኢት ፤
በእምላክነቱ ድል አልነሣውም ።
ወኢኃየሎ በክሂሎቱ ።
በከሃሊነቱ አልተዋጋም አልሠለጠነበትም ።
ወኢበምንትኒ እምዕበዩ ፤

ከጌትነቱ ወገን በምንም በምን በአምላክነቱ ድል አልነሣውም ።

እላ በትሕትናሁ ወፍትሐ ጽድቁ በትሩፋተ ምሥጢር እንግዳ ።
እንግዳ በሚሆን ተዋርዶ በሠራው ሥራ ነው እንጅ በዘየዓቢ ጥበቡ እምነ ኵሉ ጥበብ ወልባዌ ።
ከጥበብ በሚበልጥ ጥበቡ ከእውቀት በሚበልጥ ዕውቀቱ ፤ ሐተታ ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሁኖ ማዳኑ ይበልጣልና ።
ቀዳማዊ ዘውእቱ እምቀዲሙ ዘእልቦ ጥንት ቃለ እግዚአብሔር ፤ ቀዳማዊ ጥንት የነበረ በዚህ ጊዜ ተገኘ የማይባል እካላዊ ቃል ፤
ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ።
ሁሉ በሱ ሕልውና በሱ አንድነት የተፈጠረ ።
ወዘእንበሌሁስ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ እምዘኮነ ያለሱ ሕልውና ግን ምንም ምን የተፈጠረ የሌለ እስመ ቃለ ኵሉ ፍጥረት ትመስል ፍጥረታት ።
የሰው ሁሉ ቃል እንጅ የሰው ሁሉ ቃልእኮንባሕርይዋን ትመስላለት ፡ እንድም የሰው ሁሉ ቃል ባሕርይዋን ትመስላለች እኮን ፤ ወእምጣናሰ እስመ ቃለ ሰብእ ሐማሚት ወጸም ሐያዊት ።
መጠኑዋ ግን የሰው ቃል ደካማ የምትጸወልግ ናትና ወሕይወታ ምሱጥ በከመ ንሬእያ እምተሣትፎትነ ዘበኅቡዕ ፤ በረቂቅ ተዋሕዶው ባለ በሥጋ አነዋወሯ ተጠልፎ ኽያጅ ነውና ።
ኃላፊት ወማሳኒት ፤
ያኑ እንደናውቅ ኃላፊ ጠፊ ናትና ፡
ወሐዋሪት ኀበ ተኃጥአ ፡
ከመኖር ወደለመኖር እምኀበ ቦ ኀበ አልቦ ከምንት ወደ ኢምንት ኸያጅ ናትና ። ወቃለ እግዚአብሔርሰ ልዕልት ፡ እካላዊ ቃል ግን ከዚህ ሁሉ የራቀች ናት ።

ይእቲኬ እርዓያ ገጹ ፡ እግዚአብሔር አብን በመልክ የምትመስለው በባሕርይ የምትተካከለው ናት ።

ቀዳሚት ወፈጣሪት ። ቀዳማዊት ፈጣሪት ናት ወሕያውት ለዓለም ሀላዊት ።
ለዘላለሙ ሕያውት ባሕርያዊት ናት ።
ወነባሪት ዘኢትማስን የማትለወጥ ነባሪት ናት ወሶበ ኮነት ይእቲ ቃል ፈጣሬተ ወሕያውተ ወባሕርያዊተ ነባሬተ ለዓለም ይደሉ እንከ በዛቲ ግብር ባሕርያዊት ትሰመይ ሕላዌ እካለ ።

እንዲህ እንዲህ ከሆነች ባሕርያዊት በምትሆን በዚህች ሥራ ፤ ሕላዌ ፡ አካል ባሕርይ ልትባል ይገባል እስመ ትርጓሜሃ ለሕላዌ በኀበ መምህራን ነባብያን በጥይቅና ።

እስረድተው በሚተረጉሙ በመምህራን ዘንድ የሕላዌ ትርጓሜ አካል ነውና አካል ባሕርይ ነውና ባሕርይ ልትባል ይገባል ፤
ውእቱ ዘአልቦ እሠር ለባሕርይ ፤
ባሕርዩ የማይመረመር እርሱ ፤
ፈቀደ በፈቃደ አቡሁ ወበሥምረተ መንፈሱ ቅዱስ ከመ ይቤዙ ኵሎ ነፍሳተ እለ ሙቁሓን ኀበ ጽልመተ ሞት ወጥንቃቃተ ሲኦል ።

በባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሞት ባመጣው ጨለማ ተግዘው የነበሩ ነፍሳተን በሲኦል ምትግግነት ያሉ ነፍሳትን ሊያድን ወዷልና ።
በሕላዌሁ ቅዱስ ፤
ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ በተለየ እካሉ ፤
ወኀብአ ብርሃነ መለኮቱ ዘኢይትከሃል ከመ ያስተርኢ በተሠግዎቱ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ።

በፈቃደ አቡሁ ወበሥምረተ መንፈሱ ቅዱስ በተሠግዎቱ ። ባባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ከመንፈስ ቅዱስ ከፋይነት ከመቤታችን ተከፋይነት የተነሣ ሰው በመሆን ኀብአ ፤ እንድም በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው መሆኑ ሊታይ የማይቻል ብርሃነ መለኮቱን በሥጋ ሰወረ ።

ከመ ይቅረብ እምኔሁ ጸላኢ ወይብጽሕ ኀቤሁ ፡ ይቅረብ ያለውን ይብጸህ እምኔሁ ያለውን ኀቤሁ እለው ጸላኢ ዲያብሎስ ወደሱ ይደርስ ዘንድ እንድም ሰው ከመሆን የተነሣ የሰውነት ሥራ ከመሥራቱ የተነሣ ወደርሱ ይቀርብ ዘንድ ወደርሱ ይደርስ ዘንድ ። ወያምስሎ ከመ ካልዓን ሰብእ እለ ውስተ ጼዋሁ በምርኮኝነት እንዳሉ እንደ ሌሎች ሰዎች ያደርገው ዘንድ ።
ወያስተጌብሮሙ ግብር ፡

ሥራውን የሚያሠራቸውን ያስመሰለው ዘንድ ሥራውን እንደሚያሠራቸው ያደርገው ዘንድ ወያስተጌብሮ ግብር ። ሥራውን የሚያሠራውን ሰው ያስመሰለው ዘንድ ።

ወኢይፍራህ እምነ ዕበዩ ወመንክራቲሁ ሶበ ርእየ ከተእምራቱ ከጌትነቱ ወገን ባየ ጊዜ እንዳይፈራ ወበከመ ኮነ እንከ ሰይጣን በጉሕሉት ተኃብኣ ውስተ ሥጋ ከይሲ ።

ኮነ ያለውን ተኃብአ ብሎ አመጣው ፤ ሰይጣን በተንኮል በሥጋ ከይሲ እንደ ተሠወረ ።

እስከ ተሠልጠ ወጸንዓ ላዕለ ፍጥረትነ እምቀዳሚ ከጥንት ዠምሮ በባሕርያችን እስኪሠለጥን ድረስ ሐተታ ተሠልጠ ጸንዓ ማለቱ ግን ሥጋን በመቃብር ነፍስን በገሃነም ተቆራኝቶ ይኖር ነበርና ነው ከማሁ ኮነ ድኅነትነ እማዕሰር በተሰውሮተ ቃለ እግዚአብሔር በዘመድነ ።

እኛም ከፍዳ መዳናችን ቃለ እግዚአብሔር በባሕርያችን በመሰወሩ ሆነ ።

ወበተዋሕዶቱ ቦቱ ፤
ሥጋን በመዋሐዱ ሆን ፤
እስከ ቤዘወነ እምኔሁ ፤ ከሱ እስኪያድነን
ወአደኃነነ በፍትሐ ጽድቅ ወርትዕ ።
በፍትሐ ጽድቅ በፍትሐ ርትዕ አዳነን ። ሐተታ እንዳሰፈው ።

ወኮነ ከመ ኵሉ ሰብእ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ ፤
ከብቻዋ ከኃጢአት በቀር እንደ ሰው ሁሉ ሆነ ፣
ወኮነ ኵሎ ከመ ሰብእ እንደ ሰው ሁሉን ሆነ ።
ወእምድኅረ ዝንቱ ወእምቅድሜሁኒ ኢተዓርቀ እመንበረ ስብሐቲሁ ።

ከፅንስ በኋላ ከልደት በፊት ዘጠኝ ወር ካምስት ቀን በማኅፀን ሳለ ከጌትነቱ መንበር አልተለየም ። እንድም ከልደት በኋላ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር፣ ከልደት በፊት ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ከጌትነቱ መንበር አልተለየም ።

ወኢያንከር እንከ ወኢፎዱሂ እምዝንቱ ነገር ፤
ከዚህ ነገር የተነሣ አንድ ስንኳ አያድንቅ እንዳያደንቅ
ወኘሕነኒ ምድራውያን እለ ፍጡራን ኢነአምር ፍጥረተ ነፍስነ ነባቢት እምውስጠ ወሰነ ሥጋነ ።
ምድራውያን ፍጡራን የምንሆን እኛ የሥጋ ሕይወት ከምትሆን ከደመ ነፍስ ጋራ ተዋሕዳ ያለች የነባቢት ነፍሳችንን ባሕርይዋንስ እንኳ ዐናውቅም ።
በእንተ ዘትሰፍሕ መልዕልተ ሰማያት ።
ወደ ሰማይ የምትደርስ ስለሆነች ፤ ትደርስም እንደሆነ አትደርስም እንደሆነ ዐናውቅም ።

ወትሬኢ ኃይላተ ሰማያውያን ወፍጥረታተ ሉዓላውያን ሰማያውያን መላእክትን ሉዓላውያን ፍጥረታትን የምታይ ስለ ሆነች ። ታይም እንደሆነ አታይም እንደሆነ አናውቅም ።
ዘርእዩ ዳንኤል ነቢይ ወዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ወካልዓንሂ ።
እነ ዳንኤል እነ ዮሐንስ እነ ሕዝቅኤል ያዩትን ፣ በኪመ ርእዩ ይላል ። በኪመ ባለቤቶችን ማምጣት ነው እነ ዳንኤል እነ ዮሐንስ እነ ሕዝቅኤል እንዳዩ ።
ወኢትትአኃዝ ላቲ ነፍስ ወኢበምንትኒ እምግዘፈ ሥጋ ።
ከሥጋ ግዘፍ የተነሣ ነፍስ በምንም በምን አትገታም
ወኢይትበሐል እንከ እፎ ተዋሐደ ቃል በሕላዌ ሥጋ ወኢተዓርቀ እመንበረ ስብሐቲሁ ።
እንዲህ ከሆነ አካላዊ ቃል በባሕርየ ሥጋ እንደምን ተዋሐደ ከተዋሐደስ ከጌትነቱ መንበር እንደምን አልተለየም አይባልም ።
ወሶበ ኮነ ከመዝ ለነፍስተ ፍጡራን ወእፎ ፈድፋደ ይከውን ማዕከለ ፍጥረት ሽወጣሪሃ ፤
ለፍጡራን ባሕርይ እንዲህ ከሆነ በፍጥረትና በፈጣሪዋ ዘንድ የቱን ያህል መበላለጥ ይኖር ይሆን ።
ወእምድኅረዝ ከሠተ ኃይሎ ወዕበዮ ።

ወእምድኅረ ዝንቱ ወእምቅድሜሁኒ ኢተዓርቀ እመንበረ ስብሐቲሁ ብሎ ነበርና ከተወለደም በኋላ ከሃሊነቱን ጌትነቱን ገለጠ ።
ወዓዲ በተአምራት ።

ከሠተ ፣ ዓዲ ዳግመኛም በተአምራት ገለጠ ።
እንተ ገብረ በከሚተ አዕይንተ እውራን ።

እውራንን ከማብራት ወገን ባደረገው ተአምራት ፤
ወአንጽሖ እለ ለምጽ ። ለሙፃንን ከማንጻት ወገን
ወአንሥእተ መፃጉዓን ።

ዶዌያቸው የጸናባቸውን ከማዳን ወገን ፣
ወአውፅእተ አጋንንት እምድውያን ።
ከሕሙማን አጋንንትን ከማውጣት ወገን ።
ወአሕይዎ ሕሙማን ዘዘዚአሁ ሕማሞሙ ።
ዶዌያቸው ልዩ ልዩ የሚሆኑ ሕሙማንን ከማዳን ወገን ።

ወገሥጾ ነፍሳት ። ነፋሳትን ከመገሠጽ ወገን
ወሐዊር ዲበ ማይ ። በውኃ ላይ ከመሄድ ወገን
ወአጽግቦ እእላፋት እምኅዳጥ ኅብስት ።

አምስት እንጀራ አበርክቶ ለአምስት ሺህ ሰው ከማብላት ወገን ።
ወአንሥእተ ምውታን እመቃብራት ።
ሙታንን ከመቃብራት ከማሥነሣት ወገን ። ሐተታ ያሥነሣ አንድ አልዓዛርን አይደለምን ቢሉ ፣ መጽሐፍ ስም ካልጠራ ማብዛት ልማዱ ነውና ። አንድም በተአምረ ኢየሱስ እነ አብርሃምን ነቢያትን ሁሉ አሥነሥቷል ይላል ።
ወዘይመስሎ ለዝንቱ ።

ይህን የመሰለ ሁሉ ባደረገው ተአምራት ከሠተ ጌትነቱን ገለጸለ ።
ወገብረ ዘንተ ተአምራተ በእንተ ብዙኀ ግብራት በሰ አራት ነገር ይህን ተአምራት አደረገ ።
አሐቲ እምኔሃ ከመ ይነጽር ሰይጣን ዕበዮ ወከሂሎቶ ካራቱ አንዱ ሰይጣን ጌትነቱን ከሃሊነቱን ያውቅ ዘንድ ነው ፣
ከመ ይኩን ምክንያተ ለዘሀለወ ውእቱ ከመ ይግበር ቦቱ ከመ ኵሉ ሰብእ ጽሩዓን ።

እርሱ እንደ ዕሩቅ ብእሲ አድርጎ በሱ ያደርግበት ዘንድ ስላሰው ነገር ምክንያት ሊሆን ነው ።
ወካልዕታሂ ከመ ይኩን ተበቅሎተ ለእለ ርእዩ ዘንተ ተአምራተ ወኢተለውዎ ወርኀቁ እምኔሁ ወአስተርአይዎ በከሕደት ወበዕልወት በፍትሐ ጽድቅ ወርትዕ ሁለተኛ ተአምራቱን አይተው ባላመኑ መፈራረጃ ይሆን ዘንድ ነው ፣

ወሣልስታ ከመ ይኩን ጽንዓ ለእለ የአምኑ ቦቱ ፣ ሦስተኛም ላመኑበት ኃይል ይሆናቸው ዘንድ ነው ኃይለ ስተጋድሎቶሙ ።

ሊመዋጋት ጽንዕ ይሆናቸው ዘንድ ነው ።
ወራብዕታሂ እስመ ትመርሆሙ ይእቲ ለእለ ተመይጡ እምኃጉል ወተሰው ጽድቀ ።

አራተኛም ከክሕደት ወደ ሃይማኖት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ለተመለሱ መሪ ትሆናቸዋለችና ስለዚህ ነው ወዘቦነ ይገብር ምግባራተ ዘይደሉ ለሰብእ ።

ለሰው የሚሰማማ ሥራ ይሠራ የነበረ ማለት ለሰውነቱ የሚሰማማ ሥ ይሠራ የነበረ ።

እምኀዘን ፡ ያዝን የነበረ ፡ ወፍርኃት
ይፈራ የነበረ ። ወረሀብ ፡ ይራብ የነበረ
ወንዋም ፡ ይተኛ የነበረ ። ወጸዊረ ጽእለታት
ስድቡን ታግሦ ይቀበል የነበረ ።
ወዘአምሳለ ዝንቱ ። ነሣሣለትና ይህን
የመሰለ ሥራ ይሠራ የነበረ ።

እስመ ፈቀደ ውኂቱ በዝንቱ ከመ ይንሥት ጥበቦ ለሰይጣን ።

በዚህ የሰይጣንን ጥበብ ሊያፈርስበት ስለወደደ ነው እንድም ወዷልና ስለዚህ ነው ።
እስመ ውእቱ ኮነ ሶበ ይሬኢ ተአምረ ወመንክረ ይፈርህ ወይቴክዝ ።

ኮነ ያለውን ይሬኢ ብሎ አመጣው እሱ ተአምራቱን ባየ ጊዜ ይፈራ ያዝን ነበርና ።
ወይርሕቅ እምትውክልና ቦቱ ወተሣልቆት ላዕሌሁ እሱን እቆራኛለሁ ከማለት በሱ ከመዘበት ይርቅ ነበርና ።
ወአመ ርእየ ምንተኒ እምነ ሕጸታት ወጽርዓታት ይትፌሣሕ ።
የሰውነት ሥራ ባየበት ጊዜ ግን የላሜ ልጅ ያውራዬ ውላጅ ብሎ ደስ ይለው ነበርና ።
ወይትኤበይ ። ይታበይ ነበርና ።
ወይትመየጥ ኀበ ትውክልና ቦቱ ።
እሱን እቆራኛለሁ ወደማለት ይመለስ ነበርና ፤
ኳመ ሙቁሕ ውስተ እዴሁ ።
በእጁ እንደ ተያዘ እድርጎ ፡
ወምኦ እንከ ። ድል ነሣው ፡
ወነሢኦ ጥበቢሁ በዛቲ ገጸት ንሥተታት ዘዘዚአሃ ኵለንታሃ ብይንት ።
እየራሱ እየራሷ የጎላ የተረዳ መለየትን በተለየች የፈረሡች በምትመስል በሰውነቱ ሥራ ጥበቡን አፈረሠበት ።
ወተከሥተት ሎቱ ተመውኦቱ ፡
ድል መሆኑ ተገለጸችለት ።
ወጽርዓት ጥበቡ ። ጥበቡ ዛገች ።
ወጽዕቀቶ ቦቱ ስሕተቱ ወምክንያቱ እምተቃርኖተ ተአምራት ብሩሃት ወንሥተታት ከሡታት ።
የጎላ የተረዳ መፍረስን የፈረሱ የሚመስሉ ተአምራትን ከመቃወሙ የተነሣ ስሕተቱ ምክንያቱ ወለሉ አሰኘችው ፡ ሐተታ የሰውነቱን ሥራ ሲሠራ የአምላክነቱ የፈረሰ ይመስላል ፡ የአምላክነቱን ሥራ ሲሠራ የሰውነቱ የፈረሰ ይመስላልና ያንንም ንሥተታት ፡ ያንንም ንሥተታት አለ ።
ወኮነት ልማደ ንብርተ ለካህናተ አይሁድ ።

ለካህናተ አይሁድ የለመደች ሥርዓት ነበረች ፤ አንድም ኮነት ልማደ ንብርተ ፤ ሥርዓት የጸናች ሁና ነበረች ።
ከመ ይፍትሑ ላዕለ ጊጉያን ።

በበደለኞች ይፈርዱ ዘንድ ፡
ቀተልት ወሠረቅት ወፈያት በስቅለት ።
ነፍስ በገደሉ ሞትን በሠረቁ ግርፋትን ፡ በወምበዴ ስቅለትን ይፈርዱ ዘንድ የቀረው ቅጣቱ ስልት ስልት አለው ለወምበዴ ግን ስቅለት ነው ።

ወእልሆሰሰ ሎሙ ፀራዊ ከመ ዝንቱ ውእቱ ኢየሱስ ዘነሠተ ሕገ ወገብረ ተአምራት ወመንክራት በዕለተ ሰንበት ።

ሥርዓት አፍርሶ ቅዳሜ ተአምራትን ያደረገ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ጸላዒ ዲያብሎስ ሹክ አላቸው ዝንቱ ብእሲ ዘኢየዓቅብ ሰንበተ ኢኮነ እምእግዚአብሔር እንዲሉ አደረጋቸው ።

ወኮኑ ሎቱ አርድእት ብዙኃን እምነ አይሁድ ፤ ከአይሁድ ወገን ብዙ ደቀ መዛሙርት እንዳሉት ሹክ አላቸው ፡ ናሁ ኵሉ ዓለም ተለዎ ድኅሬሁ ኢተእምሩኑ ከመ አልቦ ዘንበቍዕ እንዲሉ አደረጋቸው ወእምከመ ተሰምዓ ዝ ግብር ከመዝ ይትልውዎ አይሁድ ኵሎሙ በእንተ ዘርእዩ እምዕበየ ተአምራት ዘላዕሌሁ ።

ተአምራቱ የታወቀ የተነገረ እንደሆነ በሥልጣኑ ካደረገው ከተአምራቱ ብዛት ወገን ፡ አንድም ከፍጹም ተአምራቱ ወገን ስለ እዩ መላው አይሁድ እንዲያምኑበት ሹክ አላቸው ። ዝንቱ ብእሲ ብዙኀ ተአምረ ይገብር ወእመ ኀደግናሁ ከመዝ ይመጽኡ ሰብእ ሮሜ ወይነሥኡ ብሔረነ ወሕዝበነኒ እንዲሉ አደረጋቸው ።

ወኢትረከቡ ላዕሌሁ ጌጋየ ዓቢየ ዘአንበለ ዘተንግሩ ለጲላጦስ መኰንን ።
ለጲላጦስ ከመንገር በቀር ለሞት የሚያበቃው ነገር አታገኑበትም አላቸው ።
እስመ ዝንቱ ገብረ ዲቤሁ ፅርፈተ ላዕለ እግዚአብሔር ወላዕለ ንጉሢ ።

ሰንበትን በመሻሩ ላይ እግዚአብሔርነኝ ንጉሥነኝ አለ ብላችሁ ለጲላጦስ ከመንገር በቀር ለሞት የሚያበቃ በደል አታገኙበትም ።
እስመ ውእቱ ይብል ቦ ጊዜ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ ፤ ወልደ እግዚአብሔር

ነኝ ይላልና ወልደ እግዚአብሔር ነኝ አለ ብላችሁ ፣ ወቦ ጊዜ ከመ ንጉሠ አይሁድ ውእቱ ።

የአይሁድ ንጉሥ ነኝ ይላልና የአይሁድ ንጉሥ ነኝ አለ ብላችሁ ፣ እንድም እየራሱ ለማውጣት ወልደ እግዚአብሔር እንደሆነ የሚናገርበት ጊዜ አለና እግዚአብሔር ነኝ አለ ብላችሁ ።
ንጉሥ እንደሆነ የሚናገርበት ጊዜ አለና ንጉሥ ነኝ አለ ብላችሁ ለቄሣር ከመንገር በቀር ሌላ በደል አታገኙበትም ።
ወንሕነሰ አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሣር ፤

ለኛስ ከቄሣር በቀር ያለቄሣር ሌላ ንጉሥ የለንም እንዲሉ አደረጋቸው ሐተታ እንዲሁም ባሉ ጊዜ በሥጋቸው ቄሣር በነፍሳቸው ዲያብሎስ ሰልጥኖባቸዋል ።
ወናሁ ፈታሕነ ላዕሌሁ በሞተ ስቅለት ።

ስቅሎ ስቅሎ እንዲሉ አደረጋቸው ።
ወተሰምዓ ነገር ከመ ጲላጦስ ተሰጥዎሙ በዘፈትሑ ቦቱ ላዕሌሁ ወአውሥአሙ ለሊሁ በሥምረቱ ።
ስቅሎ ቢሉት ጲላጦስ ሊያድነው ወዶ ምንተ እኩየ ገብረ በዘይመውት ብሎ እንደመለሰላቸው ታውቋል ተነግሯል ።
ወመጠወ ነፍሶ ለሞት በፈቃዱ ኅሪት ከመ ይቤዝዎ ለአዳም እኍት ።
አዳምን ከሞት ያድነው ዘንድ ባማረ በተወደደ ፈቃዱ ነፍሱን ከሥጋው ለየ ።
እስመ ሞትሰ እምደለዎ ለአዳም ስቁለ ዘበኃጣር ፣ ጨርቅ ታጥቆ ግንድ ተሸክሞ ተዋርዶ ተሰቅሎ መሞት ለአዳም በተገባው ነበር ። እንድም ተዋርዶ ተሰቅሎ መሞትስ ለአዳም በተገባው ነበር ታሪክ ኤልሳዕ መምሩን ኤልያስን ሸኝቶ የዮርዳኖስን ተሻግሮ ኢያሪኮ ገብቶ ሲያስተምር ሰው በዛ ጉባዔ ሰፋደቃ መዛሙርቱ ጸበበነ ማኅደር ንሑ ንግዝም ዕፀ ወንሕነፅ ካልዓ ማኅደረ ብለው ሄዱ እሱም መምህረ ትሕትና ነውና አብሯቸው ሄደ በዮርዳኖስ ዳር ሲቆርጡ ወተነጽላ ማኅጼሁ ወቦአ ውስተ ማይ እንዲል ከዛቢያው ወልቆ ብረቱ ከውኃ ገባ ወዝኒ ኅቡይ እግዚእየ ፣ ጌታዬ ይህም የተውሶ ጠፋ ተጨርሶ አለው ፣ የገባበትን አሳየኝ አለው አሳየው ቅርፍተ ዕፅ ቀርፎ እመሳቅሎ ከውኃው ላይ ቢጥለው የማይዘቅጠው ቅርፍት ዘቅጦ የዘቀጠውን ብረት ይዞት ወጥቷል ። እንደዚህም ሁሉ ሕማም ሞት የማይገባው ጌታ ሙቶ ሞት የሚገባው አዳምን የማዳኑ ምሳሌ ጥምቀትም የሞቱ ምሳሌ ነውና ።

በእንተ ዘተዓደወ ትእዛዘ ፈጣሪሁ ።
ከፈጣሪው ትእዛዝ ስለወጣ ፣
ወኮነ ቀታሌ ርእሱ ።
ራሱን እጥፊ ስለሆነ ።
እስመ በፈቃዱ አስተዳለወ ሞተ ለርእሱ ወዶ ራሱን እጥፊ ሁኖዋልና ፣ እንድም ራሱን ለመጉዳት ሞትን አስፈርዷልና ።

ወዘዕውቅሰ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢኮነ ምጽአቱ ወተሠግዎቱ ዘእንበለ ከመ ይፈጽም ዘረከቦ ለአዳም ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆኑ አዳምን ያገኘውን ነገር ለመፈጸም ነው ለሌላ እንዳይደለ የሚያስታውቅ የሚያስረዳ ነገር ፤

በጽድቁሰ አምጽአ ሞተ ላዕለ ርእሱ ዘድልው ላዕለ አዳም ።
በአዳም የተፈረደ ሞትን በራሱ አደረገው ።
ወተወከፎ እንከ ውስተ ሥጋሁ ።
በሥጋው ተቀበለው ።
ዘውእቱ ጠቢአቱ ፤
ያውም ጭከናው ነው ፣ ዘውእቱ ጠባይዒሁ ይላል ባሕርዩ በሚሆን በሥጋ ተቀበለው ።
እስከ ቤዘዎ እሞት ፤
አዳምን ከሞት እስኪያድነው ፤

ከመ ይከሥት ለነ በውእቱ ፍኖተ ትሩፋት ፤
በዚህ የትሩፋትን ሥራ ይገልጽልን ዘንድ ።
እስመ ውእቱ መጠወ ነፍሶ ለሞት እምድኅረ ተመክሮቱ ውስተ ዓውደ ምኵናን ።

እሱ ባደባባይ በመከራ ከተፈተነ በኋላ ተሰቅሎ ነፍሱን ከሥጋው ለይቷልና ።

ወኢተረክበ ሎቱ ጌጋይ ወኢነውር ለዘይትኬነን ቦቱ ፣
ነገር ግን ይሙት ቢቃ በሚፈረድበት ገንዘብ ይፈረድበት ዘንድ ነውር በደል አልተገኘበትም ።
ወበእንተዝ ኮነ ጲላጦስ ሰማዕተ ።
ነውር በደል ስላልተገኘበት ጲላጦስ መሰከረ ።
ወይቤሎሙ ለሕዝብ እስመ ዝንቱ ብእሲ ንጹሕ ወጻድቅ ውእቱ ወኢተረክበ ላዕሌሁ ኃጢአት ።
ጻድቅ ንጹሕ ነውና ኃጢአት አልተገኘበትምና ።
ነሥአ ማየ ወተሐፀበ እደዊሁ ወይቤ ንጹሕ አነ እምደሙ ለዝ ብእሲ ጻድቅ ወኄር ።

ወይቤሎሙና ይቤ አንድ ወገን በዚህ ሰው ደም ከሚመጣ ፍዳ ንጹሕ ነኝ ብሎ ውኃ አስመጥቶ ባደባባይ ታፀበ ።
በከመ ሰምዓ ኮነ መጽሐፍ ።
ወንጌል ነሥአ ማየ ወተሐጽበ እደዊሁ ብሎ እንደ ተናገረ ፣ ታሪክ በአፅሩግ እስራኤል ልማድ ከሀገርና ከሀገር መካከል ሰው ሙቶ የተገኘ እንደሆነ ያ ሰው ለሞተበት ስፍራ አቅራቢይ በሚሆን አገር ያሉ ሰዎች ውኃ በመንቀል ይዘው ጊደር ነድተው ከበረሃው ይወርዳሉ ፣ ቋንጃዋን ይመቷታል ትወድቃለች የዚህን ሰው ደም እኛ አላፈሰስንም ያፈሰሰውንም አላየንም ብለው ይታፀባሉ ከገዳዩ ወገን

ሲደርስ መወየብ ይጀምራል ከገዳዩ ሲደርስ ፈጽሞ ደም ይሆናል ። ምእመናንም ጥምቀትን ገንዘብ ማድረጋቸው መናገር ነው ።
ወሶበ ኮነ ከሃሌ ኩሉ ግብር በእንተ ተሠግዎቱ በፍጥረትነ ፈቀደ ሐሚመ ህየንተ ከሂሎቱ ፤
ባሕርያትንን ስለ ተዋሐደ ሁሉንም ማድረግ የሚቻለው ቢሆን የከሃሊነቱ ለውጥ የከሃሊነቱ ፈንታ ከሃሊ ሲሆን ወዶ መከራውን ተቀበለ ።
ወተትሕተ ህየንተ ልዕልናሁ ።

የልዕልናው ለውጥ ፡ የልዕልናው ፈንታ ልዑል ሲሆን ተዋረደ ።
ወሞተ ህየንተ ኃይሉ ።
የኃያልነቱ ለውጥ ፡ የኃያልነቱ ፈንታ ኃያል ሲሆን ሞተ ወእፎኑመ ማንሻ ። እንድም ከሃሊ ባለው ከሃሌ ይላል ባሕርያችንን ስለ ተዋሐደ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው እሱ ወዶ መከራ ስለ ተቀበለ ስለተዋረደ ከሞተ ፤
ወእፎኑመ ንሕነ ምኑናን ወጽቡሳን ወምስኪናን ዘኢንትመሰል ቦቱ ፤
ምኑናን ጽቡሳን ምስኪናን የምንሆን እኛ በመከራ እሱን የማንመስል እንደምን ይሆን ።

ሶበሰ ኮነ እግዚእነ ሞያ ለሰይጣን በኃይሉ መዋኢት እምኢኮነ መንከረ ።
ኮነ ያሰውን ሞያ ብሎ አመጣው ሰይጣንን ጌታችን በአምላክነቱ ድል ነሥቶት ቢሆን ባልተደነቀም ነበር ።
ወእምኮነት ዘውስቴቱ ትሩፋት ዘኢሰብሕት ወዘኢውድስት ፤
ሥራው ያልከበረች ያልተመሠገነች በሆነች ነበር እንድም እምኢኮነት ዘሰብሕት ባልተመሠገነችም ነበር ።
ትሩፋትሰ ስብሕት ዛቲ ይእቲ ፤
የምትመሠገነስ ትሩፋት ይህች ናት ፤
መዊት ላዕለ ዝንቱ ገጽ ምንከር እንግዳ ወዕጹብ ግቱ ።

ፈጽሞ ድንቅ እንግዳ በሚሆን በሰውነቱ ሥራ ድል መንሣት ነው ።
ሎቱ ኮነ ፍኖት ሰፉረ ወልብው ።
ፍኖት ለኀበ አቡሁ እንቀጽ ዘመንገለ ወላዲሁ የሚባል ጌታ ሰው ሆኖ ባጭር ቁመት በጸባብ ደረት ተወስኖ በታወቀበት በሰውነት ሥራ ድል መንሣት ነው ፤
እስከ ኃሠሠ እምኔነ ሰበዊዕ ውስተ ዝንቱ እንቀጽ ጽቡብ ።

ከኛ ወገን አንዱም አንዱ እያንዳንዱ ወደ ትሩፋት ለመግባት እስኪሻ ድረስ ፤
ወእቶሙ ውሉዳን እለ ይበውኡ ውስቴታ ፤
ወደ ትሩፋት የሚገቡ ማለት ትሩፋት የሚሠሩ ጻድቃን ጥቂት ናቸውና ።
ወሶበ ፈቀደ ከመ ይመጡ ነፍሶ ለሞት በሥምረቱ ኅሩያዊት ፈቀደ እንከ ሰይጣን ሞቅሐታ በፍሥሐ ወበሐሤት ።
በማረ በተወደደ ፈቃዱ ነፍሱን ከሥጋው ሲለይ በወደደ ጊዜ ሰይጣን ፈጽሞ ደስ ብሎት እቁራኛስሁ ብሎ ቀረበ ።

ወገሠጾ እግዚአብሔር ።
ወግድ ከኔ ፤ ከኔ ምን አለህ አለው ።
ወቀፈጾ ዘእምላዕሌሁ ምክዳን ።

ከአምላክነቱ ብርሃን ጥቂት ብልጭ አደረገበት ። ሒተታ በጸባብ መስኮት ብርሃን እንዲገባ ይላሉ ይህስ ይበዛል ብሎ የምጣድ ብልጭልጭታ ያህል ፤
ወርእየ ኃይላተ ሰማይ ድንጉጻነ በእውደ መስቀሉ ቅዱስ ።

መላእክትን በመስቀሉ ዙሪያ እንደ ሻሽ ተነጽፈው እንደ ቅጠል ረግፈው እንደ ግንድ ተረብርበው አየ ። እንድም ድኑናን ይላል አምላክነ ክርስቶስ እያሉ ሲሰግዱ ሲወድቁ ሲነሡ አየ ።
ወተጠብለለ በደዌ ፀዋግ ወፍርሃት ፍድፉድ ፤

በጽኑ ፍርሃት ተያዘ ።
ወተጠየቀ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ በእላንቱ ራእያት ።
ወቀፈጸ እምላዕሉ ምክዳን ወርእየ ኃይላተ ሰማይ ድንጉጻነ በዓውደ መስቀሉ ባለው ነገር ወልደ እግዚአብሔር እንደሆነ አወቀ ተረዳ ።

ወእምሰምዐ እንተ ሰምዓ ኮነ አብ እምሰማይ በክሡት እመ ጊዜ ጥምቀት በፈለገ ዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ አብ ከሰማይ መጽቶ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ በጉባዔ በዮርዳኖስ ከመሠከረለት ምስክርነት የተነሣ ፤
ወዓዲ በላዕለ ደብረ ታቦር ፤
ዳግመኛ በደብረ ታቦር ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ከመሠከረለት ምስክርነት የተነሣ ።
ወእምዝ ልህበ ልህበተ እምኔሁ ።

እቁራኛስሁ ብሎ ከመቅረቡ የተነሣ ፤ የባሕርይ ልጅ መሆኑን ከማወቁ የተነሣ መጋልን ጋለ መቀኩሰን ተኩስ ፤
ወተረፈ ቅውመ ኀበ ውሣጤ ነፍሳት ዘኢይክል ያንቀለቅል ፤
በአሳት ዛንጀር ታሥሮ በነፋስ አውታር ተይዞ ወዲያና ወዲህ ማለት የማይቻለው ሆኖ ቁሞ ቀረ ።
ወኮነት ምግባራቲሁ ኩሉ ወተቃውሞቱ ዘምስለ እግዚእነ ሥዕልተ በቅድሜሁ ።
የሚሠራው ሥራ ሁሉ ከጌታ ጋራ የሚቃወመው መቃወም ሁሉ በፊቱ እንደ ሥዕል እንደ መስታዋት ተሥሎ ተቀርጾ ታየችው ።

ዘከመ ተቃውሞቱ እንተ ተቃወመ ወትዕግልተ እንተ ተዓገለ ።

እንደ ተቃወመው መቃወም እንደ ቀማው ቅ ምያ ያለ ።

እንዘ ያስተነትን ዘይመጽእ ሳዕሌሁ እመቅሠፍት በእንቲአሃ ።

ስለ ስድቡ ከመቅስፍት ወገን በሱ የሚመጸበትን ሲያወጺ ሲያወርድ እንደ ትቢያ ያበነኝ እንደ ጢስ ያተነኝ ይሆንን እያለ ።

ወእምዝ ተዘከረ ክብራተ እንተ ኮነት ሎቱ ቀዳሚ ምስለ መላእክት ።
ከዚሀ በኋላ ከመላእክት ጋራ ያደርጋት የነበረች ክብሩን አስቦ ። ሐተታ ተቀብቷል ቢሉ የተመች አልተቀባም ቢሉ ቢጸና ።

እስመ ውእቱ በሥምረቱ ጸነ እስከ ወድቀ ወኃደገ ሎቱ እግዚአብሔር ሥልጣኖ እንቲአሁ ይግበር ባቲ ዘፈቀደ ።

በሥምረቱ ብሎ ነበርና በምን ዐውቆ ትሉኝ እንደሆኑ የወደደውን እንደ ወደደ ያደርግባት ዘንድ በተፈጥሮ የተሰጠችውን ግዕዛንኑ አልነሣውም ። ወውእቱ ከሃሊ በነሚኦታ እምኔሁ ።
ግዕዛኑን ነስቶ እንደ ሥዕል እንደ እንስሳ ሊያደርገው የሚቻለው ሲሆን ።
ወምግባራቲሁ እንተ ቀደመት ላዕሌሁ ዘምስለ አይሁድ ።
በአይሁድ አድሮ ሲሠራው የነበረውን ሥራውን አስቦ ወተአግሦተ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ዘበእንቲአሃ። ምንም ዚዘድለው እግዚአብሔር ታግሦት እግዚአብሔር እቡን መታገሡን አስቦ ።
ወአስተዓበዮ መጠነ ይፈድዮ ለወልደ እግዚአብሔር ለወልደ እግዚአብሔር የሚከሰውን ካሳ አበላለጠ
ሰማይ ወዘውስቴቱ ።
ሰማይ የኔ ገንዘብ ሁኖ በሰማይ ያሉ ፍጥረታትም የኔ ገንዘቦተ ሁነው ፣ እንድም ከመ ሰማይ ወከመ ዘውስቴቱ እንደዚሀ ሰማይ ያለ ሌላ ሰማይ ኑሮ ያየኔ ገንዘብ ሁኖ በዚህ በማይ እንዳሉ ፍጥረታት በዚያም ኑረው እኒያ የኔ ገንዘቦች ሁነው ።
ምድር ወዘዲቤሃ ፣
ምድር የኔ ገንዘብ ሁና በምድርም ያሉ ፍጥረታትም የኔ ገንዘቦተ ሁነው ፣ እንድም ከመ ምድር ወከመ ዘውስቴቱ ፣ እንደዚህ ምድር ያለ ሌላ ምድር ኑ ያ የኔ ገንዘብ ሁኖ በዚህ ምድር እንዳሉ ፍጥረታት በዚያም ኑረው እኒያ የኔ ገንዘቦች ሁነው ።
ኢይከውኖ እምጣነ ቀዊሞቱ ቅድመ ጲላጦስ ቅጽበተ ዓይን ኀድግሰ ዘኮነ ቅድመ ዝንቱ ወድኅሬሁኒ ክዚህ አስቀድሞ ከእንግዲህም ወዲህ የሚደረገውን ተወውና ዓይን ተከድኖ እስኪገለጽ ድረስ በጲላጦስ ፊት ስላቆምሁት ካሣው ሊሆኑት አይበቁም ብሎ አበላለጠ ።

ወሶበ አእመረ እግዚአብሔር ሕሊናሁ አቅለለ ሎቱ ዕፀበ ወላህበ ።
እንዲህ ማለቱን እግዚአብሔር ባወቀ ጊዜ እስራቱን አላላለት ግለቱን አቀዘቀዘለት ።
ከመ ይኩን ቀዊሞቱ በፍድየት ሀየንተ ፈቃደ ሥምረቱ ።

ወዶ ነፍሳትን እለቃለሁ ማለቱ በካሣ ይሆን ዘንድ በግድ ቀማኝ እንዳይል ። እንድም ጌታ ስለ ወደደለት እናወሩ በዚህ ዓለም ይሆን ዘንድ ።
ወሶበ ፈትሐ እማዕሰሩ ወጠፍአ ላህቡ ወቆመ ቅድመ እግዚእነ እንዘ ይገርር ወይሰግድ ወያስተበቍዕ ።

እስራቱን ባላላለት ግለቱን ባቀዘቀዘለት ጊዜ እየተገዛ እየሰገደ እየማለደ በጌታ ፊት ቆመ ።
ከመ ይዕትት እምኔሁ ሙስና ።
ጥፋቱ ይርቅለት ዘንድ ። እንድም ያእትት ይላል ጥፋቱን ያርቅለት ዘንድ ።
ወያብሖ ለነቢር ውስተ ምድር ።
በዚህ ዓለም ለመኖር ያሰናብተው ዘንድ ።
ወያንሥእ እደዊሁ እምነ አዳም ወዘርዑ ።
እሱም ቍራኝነት ከአዳም ከልጆቹ ያርቅ ዘንድ ።
እለ ተጋብኡ ውስተ ሞቅሕ በፈቃድ ዘእንበለ እእምሮ ።

ሳያውቁ ወደው በሠሩት ኃጢአት ። እንድም በነቢብ በገቢር ሳይሆን በሐልዮ በሠሩት ኃጢአት በቁራኝነቱ ካሉ ከአዳም ልጆች ቍራኝነትን ያርቅ ዘንድ ፤
ወተሠጥወ ስእለቶ ። ልመናውን ተቀበለው።
ወአዕረጎሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለዙሉ ዘርዑ እምሲኦል ። አዳምን ልጆቹን ከሲኦል ወደ ገነት አወጣቸው ሐተታ ዲያብሎስም ፈጽመህ ካጠፋኸኝማ ያንተስ ጠላት የኔስ ወዳጅ በምን ይታወቃል ከፈቃድህ የወጣ ፍርፋሪ ለቅሜ ልኑር ብሎ ለምኖታል ።
ወአግብአ ኅበ ዘቀዳሚ ንብረቱ ውስተ ገነተ ፍግዓ ተድላ ደስታ ወደሚያደርግበት ወደ ቀደመ ቦታው ወደ ቀደመ ማዕርጉ መለሰው ።
ወአኅለፎሙ ለጻድቃን ምስሌሁ እምኃጕል ፤
ጻድቃንን ከሱ ጋራ እንደሱ ከሲኦል አውጥቶ ገነት አገባቸው ።
ኀበ ፍትሐ ጽድቅ ወርትዕ ፣ ቀድሞ ፍትሐ ጽድቅን ፍትሐ ርትዕን ወደሰሙባት ኋላ በፍትሐ ጽድቅ በፍትሐ ርትዕ ወደ ወጡባት አገባቸው
ወኃደጎሙ ለኢኩያን ህየ ውስተ ትውክልና ፤
እኩያን ነፍሳትን ግን በሲኦል በቁራኝነት እንዳሉ ተዋቸው ።

ምስለ መላእክቲሆሙ እስከ ዕለተ ደይን ፥ ከመላእክቶቻቸው ከአጋንንት ጋራ ፥ እንዲሁም ከፈርዖን ከሄሮድስ ጋራ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በሲኦል ተቀምጠው ።

ወእምድኅረዝ ተንሥአ እሙታን ከመ ይምሐረነ ተንሥኦ ሥጋቲነ እምድኅረ ሞት ።

አጋንንትን ድል ነሥቶ ነፍሳትን ከሲኦል አውጥቶ ብት [illegible] [illegible] የኛን ትንሣኤ ያስረዳ ዘንድ ተነሣ ። ለግሀል ወለደይን ወለፍትሕ ፥
ግልጽ ፤ ለጻድቃን የሚደረገው ፥ ደይን በኃጥአን የሚፈረደው ፥ ፍትሕ የወል ነው ።
ወዐርገ ውስተ ሰማያት ፤
በተነሣ በአርባ ቀን ዓረገ ፤

ከመ ያብጽሕ ለነ ዕርገተ ጻድቃን ንጹሐን እምድኅረ ትንሣኤ ኀበ መንግሥት ዘድልው ሎሙ ።
ዕርገት እምድኅረ ትንሣኤ ፤ ከትንሣኤ በኋላ ጻድቃን በነፍስም በሥጋ በብርሃን ወደ ተዘጋጀላቸው ወደ መንግሥት ሰማያት መግባታቸውን ያስረዳ ዘንድ ዓረገ ።
ወእምዝ ፈነወ ሎሙ መንፈስ ቅዱስ ።
ዓረገ ባሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ሰደደላቸው
ከመ ንትመራሕ ቦቱ ኀበ ሐዊረ ፍኖት ፤
ወደ ትሩፋት ሥራ እንመራበት ዘንድ ማለት ትሩፋት እንመራበት ዘንድ ።
እንተ ትወስድ ኀበ ሕይወት ወመድኃኒት ፤

ፍኖት ላለው ወደ ደገኛው ልጅነት ወደ ትንሣኤ ዘክብር የምታደርስ እለ ፤ ፈነወ ላለው ዋዌ ፥ የዓረፍትን ልጅነት ወደ ደገኛው ልጅነት የሚያደርስ እለው ፤ ወናሁ ተጠየቀ ወጸንዓ በቀኖናተ ዝንቱ መጽሐፍ ንጹሕ ፥ ከፈታደ ሥጋ ንጹሕ የሚሆን የዚህ መጽሐፍ በቀኖናት በቀኖናትነቱ ታወቀ ተረዳ ።
ወብዙኅ ተኀሥሦ መፍቅድ ኀበ አንብቦቱ ለዘኮነ ልቡ ወግዕምረ ።

ብልህ አስተዋይ የሆነ ደቀ መዝሙር ከተመለከተው ዘንድ ልቡና የሚሻው ብዙ ምሥጢር አለበት ።

ስድስተኛ ጉባኤ ፤

መገለጡ ሥርዓት ፥
ሦስተኛውን ሥርዓት ብለውታል ሥርዓት ይባላል
ወሥርዓት ዝንቱ መጽሐፍ ክቡር ፤
ክቡር የሚሆን የዚህ መጽሐፍ ሥርዓቱ ፤
ይእቲኬ አንብቦቱ በኵሉ ጊዜ ፥

ኵሉ ጊዜ በኵሉ ጊዜ ይላል ሁልጊዜ እሱን መመልከት ነው እመኒ እንዘ ትነውም ወእመኒ እንዘ ትንቅሕ እመኒ እንዘ ትነብር ወእመኒ እንዘ ትትናግእ እመኒ እንዘ ትቀውም ወእመኒ እንዘ ተሐውር ኢትርሳዕ ተዘክሮተ እግዚአብሔር አምላክነ በበኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት እንዲል ፥

ወኃዲግ ሕሊናት ለዓቂበ አቅማሪሁ ወተአምሪሁ ፥ ሰንጠረዡን ቁራኛውን ለማወቅ ሕሊናትን ጨልጠ ገርኝቶ መስጠት ነው ፥ እንድም መብል መጠጥን መተው ነው፤እንድም ሕሊናትን፥ማጽናት ነው ኃዲገን ጥንተ ነገሩ እንዲል ፤

ወተአዝዞ ቦቱ ፥ በሱ ጸንቶ መኖር ነው
በጠይቆ ወበገቢር ወቀዊም በኵሉ ትእዛዛቲሁ ፥
በመረዳት ፥ በሥራ በትእዛዙ ሁሉ ጸንቶ መኖር ነው
በቃል ፥ ባነጋገር፥
ወበምግባር ፥ በሥራ ፥
ወተመያይጦ ኀበ ጽንዓቱ ፥

ከጸናም ዘንድ መላልሶ መመልከት ነው ፥ ለእመ ረከብከ ቀለመ ጸዋግ ተመያየጥ ዐሥርተ ወከልኤተ ጊዜያተ ወኢትፍቅድ ኃሊፈ ቀጽል እምኔሁ እንዲል ፥
ወምሳሌያቲሁ ዘምሱል ኀበ ትርጓሜያት ፥
የተመሰለውን ምሳሌውን ወደ ትርጓሜ ሲያፍልሱ መኖር ነው ፤ እንድም ዘምሉስ ይላል አብነት ወደ ትርጓሜ የተመለሰውን ምሳሌውን ማወቅ ነው ፥
ዘጽሕፍት ፥ በብራና ፥
ወዕውቅት ፤ በልቡና ታውቃ ያለች
ወበውእቱኬ ይትበየን ለአንባቢ መሴልዩ ኵሉ ኃይለ ቃሉ ፤

በዚህም ለተመልካች ደቀ መዝሙር የነገሩ ምሥጢር ብልት ብልቱ ይታወቃልና ስለዚህ ነው ፥ እንድም ምሊሳዩ ኵሉ ኃይለ ቃሉ ይላል የነገሩ ምሥጢር መለያያ መለያያው ይታወቃልና ስለዚህ ነው
በብሩሀ ብያኔ ፥ በጎላ በተረዳ መለየት
ወይነሥእ በእስተብዖቀ ጥይቅና ወተፍጻሜተ ዘሀሎ ውስቴቱ ፥

በሱዋ ያለውን በመመልከት ዕውቀትን በመረዳት ገንዘብ ያደርጋልና ስለዚህ ነው ፤
እስከ ደኀሪት ነገር ፥
ሳብዕ አርእስተ ነገር ያለው እስኪፈጸም ድረስ እንድም ሙላው እስኪፈጸም ድረስ ።
ወናሁ ተጠየቀ ሥርዓቱ ፥

የዚህ መጽሐፍ ሥርዓቱ ታወቀ ተረዳ ፤ እንድም ወጸንዓት ንበቱ ይላል እሱን በመመልከት ጸንቶ የመኖሩ መጽናት ታወቀ ተረዳ ወጸንዓት ንብረቱ ይላል እሱን በመመልከት መኖሩ ታወቀ ተረዳ ፤
ወራብዑ ትእምርት ፥
አራተኛውን ስም ብለውታል ስም ይባላል ስምዮት ትእምርት ይላል ፥
ወትእምርተ ዝንቱ መጽሐፍ ክቡር ወንጌል ።

ክቡር የሚሆን የዚህ መጽሐፍ ስሙ ወንጌል ነው ወንጌል ብሂል በልሳነ ጽርእ ወትርጓሜሁ ስብከት ወንጌል ማለት በጽርእ ቋንቋ ብሥራት ስብከት ማለት ነው ።
እስመ ተሰብከ ውእቱ

ወልደ እግዚአብሔር እንደነገሠ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንዲጠፋ ተናግራለችና ወንጌለ መንግሥት እንዲል ወደ ግእዝ ቢመልሱት ወንጌል ማለት ስብከተ ማለት ነው እለ ።

በእንተ ትስብእተ ቃለ እግዚአብሔር በዘመድነ በና ሣሕርይ ቃለ እግዚአብሔር ሰው መሆኑን ተናግራልና አንድም ሰው መሆኑ ተነግሮበታልና ወኀድረተ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ ወውስቴትነ ፥ መንፈስ ቅዱስ በኛ ማደሩን ተናግራልና ። አንድም መንፈስ ቅዱስ በኛ ማደሩ ተነግሮበታልና ። ላዕሌነ ወውስቴትነ ማለቱ በነፍስ በሥጋ ሲል ይደጋግመዋል ዓዲይከ ዛቲ ብሥራት እንተ ባቲ ደለዎሙ ለውሉደ ሰብእ ከመ ይኩኑ ታቦተ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን ምእመናን የነቁበት የተገባት ወንጌል ደግ ሕግ ናት ።
ወማኀደረ መቅደሱ ። ልዩ ማደሪያው ይሆኑ ዘንድ ወኮነ ሎሙ ዘይበዝኅ ክብር በክብረ ዝንቱ ዕበይ ።
ለወንጌል ደገኛ ፍጹም ክብር ተሰጣቸው ።
አ ለዝንቱ ክብር ዓቢይ ወኂሩት ዘእንበለ መሥፈርት ።

ፍጹም የሚሆን ይህ ክብር ልክ መጠን ወሰን ድንበርየሌለው ቸርነቱ ምን ይረቅ ምን ይጠልቅ አ ወዮ እንደምን ያለ ረቂቅ ነው ። አንድም ፍጹም ለሚሆን ለዚያ ክብር ወሰን ድንበር ስሌለው ለቸርነቱ እንክሮ ይገባል ።
ወዜነወነ ካዕበ ተሣህሎተ እግዚአብሔር ልዑል ለደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ።
ልዑል እግዚአብሔር እኛን ይቅር ማለቱን ነግሮናልና ።
ወሰርየ ጌጋይ ።
ተኃድገ ለከ ኃጢአትከ ተኃድገ ለኪ ኃጢአትኪ ማለትን ።
ወአብጥሎ ዙነኔያት ።

ኢትጥዓም ኢትልክፍን ኢትግሥሥን ማሳለፋን ።
ወሰቢረ ሦከ መስሐቲ ጸላዒ ።
ዲያብሎስ የሚያሠራቸው እኩያት ፍትወታት ኃጣውእን ድል መንግቱን ።
ወድክመተ ትዝህርቱ ።
ዲያብሎስን በሞስቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል መንግቱን ነግሮናልና ።
ወዓዲ ዘበቍዓነ ቦቱ በጸውዖትነ ውሉደ ፤
በጸውዖቱ ውሉደ ብሎ ውሉድ እኛን በመጥራቱ እኛን የጠቀመንን ጥቅም ነግሮናልና አንድም ውሉድ ይላል ውሉድ እኛ እሱን በመጥራታችን የጠቀምነውን ጥቅም ነግሮናልና ።
ወፍግዓ ዘድልው ለነ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ወሕይወት ለዝሉፉ ።

በማያልፍ ሕይወት በመንግሥተ ሰማያት ተዘጋጅቶልን ያለ ተድላችንን ነግሮናልና ፤ ወሕይወተ ይላል ፍግዓ ላለው ። በመንግሥተ ሰማያት ተዘጋጅቶልን ያለ ተድላችንን የማያልፍ ሕይወታችንን ነግሮናልና ስለዚህ ነው ።
ወናሁ ተበየነ ትእምርቱ ።
እነሆ ስሙ ታወቀ ተረዳ ፤
ወምክንያተ ስሙ ።
ወንጌል የተባለበትም ምክንያት ታውቀ ተረዳ ።

ወኃምስ መሠረት ፤ እምስተኛውን መሠረት ብለውታል መሠረት ይባላል ። እምእይቱ ይላል እብነት ፤
ወመሠረተ ዝንቱ መጽሐፍ ክቡር ፤
ክቡር የሚሆን የዚህ መጽሐፍ መሠረቱ መሠረትነቱ በኀበ እግዚአብሔር ዓቢይ ወ እዚዝ ።
ዓቢይ እዚዝ የሚሆን እግዚአብሔር ነው ።
ወኮኑ ሎቱ ፬ቱ ጸሐፍት ፤
አራት ጸሐፍት አሉት ፤
፪ቱ እምኔሆሙ ዘእምሐዋርያት ፲፪ቱ ወ፪ቱ እለ ኃረዮሙ እግዚእነ እምዙሉ አርድእት ወሰመዮሙ ሐዋርያት ፤
ከአራቱ ሁለቱ ከአምስት ገበያ ሰው መርጦ ክሾማቸው ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ወገን ናቸው ፥
ወውእቶሙ ማቴዎስ ወዮሐንስ ፤
ሁለት የተባሉትም ማቴዎስ ዮሐንስ ናቸው ፤
ወ፪ቱ እምኔሆሙ እምአርድእት ማርቆስ ወውእቱ ዘኮነ ረድእ ለጴጥሮስ ፥

ከሁለቱ አንዱ የጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ማርቆስ ነው ወካልኡ ሉቃስ ወውእቱኒ ዘኮነ ረድእ ለጳውሎስ ፤ ከሁለቱ አንዱ የጳውሎስ ደቀ መዝሙር ሉቃስ ነው ወጸሐፉ እንከ ወ ስተ ዙሉ አህጉር ርኁቃት ፥

በቦታ ተለያይተው በርኁቃት አህጉር ጻፉ ። ሐተታ ማቴዎስ በፍልስጥኤም ይምሮ በሀንድ ይጨርሰዋል ወጠና በፍልስጥኤም ወፈጸማ በሀንድ እንዲል ማርቆስ በግብጽ በሮምም ይላል ሉቃስ በመቄዶንያ ዮሐንስ በኤፌሶን ሁነው ጽፈዋል ፤
ወበአዝማን ውሉጣት ፥
በልዩ አዝማን ጻፉ ፤ ሐተታ ማቴዎስ ጌታ ካረገ ስምንተኛው ተፈጽሞ ዘጠነኛው ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ዘመን ፤ ማርቆስ ጌታ ካረገ ዐሥራ አንደኛው ተፈጽሞ ዐሥራ ሁለተኛው ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ ባራተኛው ዘመን ፤ ሉቃስ ጌታ ካረገ ሀያ አንድ ተፈጽሞ ሀያ ሁለተኛው ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር

በነገሠ ባሥራ አራተኛው ዘመን፤ዮሐንስ ጌታ ካረገ በሠላሳ በሠላሳ አምስትም ይላል ፤ ኔሮን ቄሣር በነገሠ በሰባት በስምንትም ይላል ። ሰባት ቢሉ ሲፈጸም ስምንት ቢሉ ሲጀመር ፥

ወጸሐፉ በልሳን ዘዘዚአሁ ፥ ልዩ ልዩ በሚሆን **ቋንቋ ጻፉ** ፤ ሐተታ ማቴዎስ በዕብራይስጥ ፥ ማርቆስ **በሮማይስጥ** ሉቃስና ዮሐንስ በዮናኒ ፥ ዮሐንስን **ለይቶ በልሳነ ጽርእ** የሚል አብነት ይገኛል እንደ **[illegible] እንደ [illegible] ጥቂት ጥቂት** የልሳን መለያየት **ነው ወኮነ ኃይለ ቃሎሙ** ውስተ ፍጻሜ አሐዱ ፥ **[illegible]** የነገራቸው ምሥጢር ፩ ሆነ **[illegible]** ፥
[illegible] ነገር በመረዳት ነው ።
[illegible] ፥

[illegible] እንደ ያደረጉ ወንጌል ደግ ሕግናት ፤ **ወተሰፍሐት [illegible] ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ወንጌል [illegible] ተነገረች** ፥

ተጸሐፈት ፤ በብራና ተጻፈች
ወተለክነት ፤ በልቡና ተቀረጸች
ዘእንበለ ተውላጥ ወተሌልዮ ፥
ጥቂት ጥቂት ከመለወጥ ከመለየት በቀር ጥቂት መለዋወጥ **መለያየት** ሳይቀር አንድም እንደ ማቴዎስ **እንደ** ማርቆስ መለየት መለወጥ ሳይኖር ያለመለወጥ **ያለመለየት** ፥
ወሶበ ነበረ መሠረቱ ኀበ ባዕሉ ፤

[illegible] ባለቤቱ እንደሆነ እነሆ ታወቀ ተረዳ ፥
ወጸሐፍቲሁ ፥ አራት ጸሐፍት እንዳሏት **ታወቀ** ተረዳ ተነገረ ፥
[illegible] ምስማክ ፥
ስድስተኛውን ምስማክ ብለውታል ምስማክ ይባላል
[illegible] ዝንቱ መጽሐፍ ክቡር ፥
ክቡር የሚሆን የዚህ መጽሐፍ መክዳንቱ ፥

ውእቱ ለአይ ግብር ይሜኒ ወለአይ ገጽ አመክፈ**ልት ጥበብ ዘይፈቅድ** ልብ ወየኃሪ ።
ልብ ከሚሻው ጥበብ አድል ወገን ከሥራ ክማናቸ**ውም ሥራ** ክነገር በማናቸውም ነገር ይመች እንደሆነ **እሱም ምስማክ** ዝንቱ መጽሐፍ ክቡር ወፈቂዶቱ **[illegible]** ኀበ ተጠብቦተ ልብ ፤

ክቡር የሚሆን የዚህ መጽሐፍ መክዳንቱ እሱን መ**ምሃሩ ልቡናን ወደማራቀቅ** ያደርሳልና ስለዚህ ነው **[illegible] ሥርጉት መንበረት** ሉዓላዊ ወእስተጋብእ በተ**ግባር ፍጻሜት ዘበውስቴታ** ይበጽሕ ኀበ በቍ**ዔት [illegible]** ።
[illegible] እዝናት በእሷ ያለውን በመመልከት ወደ **ፍጻሜ ጥቅም ያደርሳልና** ስለዚህ ነው ።
ወይፈቅድ ዘሀሎ ውስቴታ ምልአተ ወተፍጻሜተ **[illegible] ያለ ደቀ መዝሙር** ዕውቀትን መረዳትን ገንዘብ ያደርጋልና ስለዚህ ነው ። አንድም ይትፈቀድ በሷ ያለ ዕውቀት መረዳት ይገኛልና ስለዚህ ነው ።
ወውእቱ እስመ ነገር እምላካዊ አመ ነሢኢቱ ወአፍልሶቱ በሕሊና ሠናይ ይፈልስ ውስተ ነፍሳት ንጹሐን እሙን ልባዌ ኀበ ተወክፎ ።
እሱም እምላክ ያስተማረው የእምላክን ነገር የሚናገር ወንጌል መምሩ እበሳበታለሁ እጠጣበታለሁ ሳይል በሚያስተምርበት ጊዜ ደቀ መዝሙር እሾምበታለሁ እሸልምበታለሁ እከብርበታለሁ ሳይል በሚማርበት ጊዜ መምር እንዳያውቅ ከመሆን ደቀመዝሙር እንዲያውቅ ወደመሆን ደርሶ ይገልጻልና አንድም እምነ ለባዊ ኀበ ተወካፊ ከአስተዋይ መምር ወደብልህ ደቀመዝሙር ደርሶ **በንጹሐት** ነፍሳት አድሮ ይኖራልና ስለዚህ ነው ። **ወይመርት ውስቴትነ** ሥርቀተ እስከ ይቀውም ውስቴትነ እምነ አርአያ እግዚአብሔር ቈመተ ዘበአማን ከአርአያ እግዚአብሔር አሰጥቶ በኛ ዘንድ ፈጽሞ እስኪረዳ በኛ ሙገለጽን ይገለጻልና ስለዚህ ነው ። በአስተርክቦ ልቡናዊት ፤

ልቡናን አንድ በማድረግ በአስተርክቦ ልቡና ይላል ሕሊናን አንድ በማድረግ ።

ዘውእቱ ሊቀ ኵሉ ትሩፋት ፥ ይኸውም የትሩፋት አበጋዝ የሚሆን ሕሊና ነው ።
ወሶበ ኮነ ውእቱ ክማሁ ኮነ እንከ ንሕነኒ ድልዋነ ለነሚአ መንፈስ ቅዱስ በረድኤት እምላካዊት ወበእንተ ዝንቱ ይደሉ ላዕሌነ ንብረት ለዘሉፉ በንጽሕና ወበኂሩት ።
እንዲህ ክሆነ ከእምላክ ዘንድ በሚገኝ ረድኤት መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ነቅተን ተግተን ስለዚህ በንጽሕና ጸንቶ መኖር ይገባናል ።
እንተ ባቲ ኮነ ድልዋነ ለተመጥዎ ሕግ እምላካዊ ወመንፈሳዊ ፥ እምላክ ያስተማረውን መንፈስ ቅዱስ ያጻፈውን ሕግ ለመቀበል በበቃንበት በረድኤት እምላካዊት ኮነ ድልዋነ ለመንፈስ ቅዱስ ፤ ዘቦቱ ኵሉ ነበበ በልሳን ዘዘዚአሁ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ፤
ሰው ሁሉ በሰባ አንድ ቋንቋ በአራቱ ማዕዘን የተናገረበት ብሎ ለሕግ ቀጸለ አንድም በአራቱ ማዕዘን ያለ ሰውን ሁሉ በሰባ ሁለት ቋንቋ ያናገረው በተሰፋ መንፈስ ቅዱስ ።
በተሰፋ መንፈስ ቅዱስ በሀብተ መንፈስ ቅዱስ በፍተ መንፈስ ቅዱስ ይላል አብነት በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ፤ ዓዲ አንቅሐነ ፈጣሪ ኀበ አእምሮ ቅድምናሁ ወተድኅሮቱ ።
ዳግመኛ ፈጣሪ ቀዳማዊነቱን ደኃራዊነቱን ወደ ማወቅ አነቃቃን ።
ይትባረክ ወይትለዓል ፥ ይክበር ይመስገን በልብ መታሰቡ በቃል መነገሩ ከፍ ከፍ ይበልና ፥ ወኀበ ልሒኮተ ፍጥረቱ መንክር ።

ድንቅ የሚሆን ፍጥረቱን በልጅነት ማደሱን ወደ ማወቅ እንቃቃን ።

ወተከሥቶ ልቡና ጥበቡ ልዕልት ወብርህት ፤

ልዕልት ብርህት የምትሆን የሥጋዊን ዕውቀት መገለጽን ወደማወቅ እንቃቃን ፤
ወናሁ ተከሥተ ምስማከ ዝንቱ መጽሐፍ ፤
እነሆ የዚህ መጽሐፍ መከዳንቱ ታወቀ ተረዳ ፤
ለእይ ገጽ ወለአይ ግብር ይኄይስ
ከሥራ ብማናቸውም ሥራ ከነገር በማናቸውም ነገር ይመች እንደሆነ ።

ሰባተኛ ጉባኤ

ወሳብዕ አርእስተ ነገር ፤
ሰባተኛውን ክፍለ ነገር ብለውታል ክፍለ ነገር ይባላል
ወአርእስተ ነገረ ዝንቱ መጽሐፍ ክቡር ፤
ክቡር የሚሆን የዚህ መጽሐፍ የነገሩ ክፍል ፤
እስመ ይእቲ ብይንት፤ የተለየች ናትና
ወውስቴታ ብያኔ ክሡት ፤

በሷም የጎላ የተረዳ መለየት አለና ስለዚህ ነው
በቃል ፤ በነገር ፤ ወበግቢር፤ በሥራ
ሁለት አርእስት ተናገረ ። ለሁለቱም ያመጣል ፤
በቃልሰ እስመ ይእቲ ትነግር በእንተ ልደቱ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ እምእግዝእትነ ማርያም ድንግል ንጽሕት ወአንሶስዎቱ ውስተ ዓለም ፤
በቃል ያልሁት ንጽሕት ንዕድት ክብርት ከምትሆን ከመቤታችን መወለዱን በዚህ ዓለም ፴ ሦስት ዓመት ከአራት ወር ከዐሥር ቀን መኖሩን ትናገራለችና ስለዚህ ነው ።
ወትኤዝዝ ኀበ ምግባራት ንጹሐት ወመሥመርያት
ንጹሐት መሥመርያት የሚሆኑ ምግባራትን ታዛለትና ስለዚህ ነው ፤
ወታሌቡ ዓዲ በጥይቅና ተስፋ በውሄበ ሕይወት ፤
ዘለዓለም ዘድልው እምነ ሠናያት ደኃርያት ፤
ዳግመኛ በኋላ ዘመን ከሚገኝ ከበጐ ነገር ወገን ተዘጋጅቶ ያለውን የማያልፈውን ድኅነት በመስጠት የተስፋውን መረዳት ታስረዳዋለችና ስለዚህ ነው።
ወታዜክር ፈሪሃ ኵነኔ ወበቀል ዘበጽድቅ ፤
በእውነት የሚደረግ ፈሪሃ ኵነኔን ፈሪሃ በቀልን ታሳስባለችና ስለዚህ ነው ፤
በአምጣነ ምግባራተ ሃይማኖት ፤
በሚሠሩት ሥራ መጠን ፤
ወእንቦስዎት ውስተ ዓለም ኃላፊ ፤
ልብስን አንጽቶ ሠናፊልን እንሰርቶ አምሞ ጠምጥሞ መንደር ለመንደር በመዞር መጠን ፤
ወፈቂድ ኀበ ነገር እኩይ ፤
ክፉ ነገርን በመውደድ ታዜክር እንድም ክፉ ነገርን በመውደድ መጠን ፤
ወሐሊናት ርኩሳት ፤
ጉዳት ያለበትን ነገር በመውደድ መጠን ፤

ወቃላተ ጕሕሉት ፤
ክዳት ተንኮል ያለበትን ነገር በመውደድ መጠን ታዜክር ፤
እስከ ተፍጻሜተ ዝንቱ ፤
ሳብዕ አርእስተ ነገር ያለው እስኪፈጸም ፤
ወኀበ ማኅለቅቱ ፤ መላው እስኪፈጸም
ወበግቢርሰ እስመ ለለ፩ዱ እምሰባክያን ክፈለ ምዕራፈ ዚአሁ እምዕራፈ ካልኡ ፤

ቃል ላለው ጨርሶ ግቢር ላለው አመጣ ፤ በግቢር ያልሁት ከአራቱ ወንጌላውያን እንዱም አንዱ እያለ አንዱም አንዱ ከባልንጀራው ምዕራፍ የራሱን ለይቷልና ፤

እምነ ፍኖት ነዊህ ወኀጺር ፤
ረጅሙን ከረጅም አጭሩን ካጭር ፤ አንድም ረጅሙን ካጭር አጭሩን ከረጅም ።
ዘእንበለ ኃይለ ቃል ፤

ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ካለው በቀር በዚህ አይለያዩም
ወተአምራት ፤ በረከተ ኅብስትን ፤
ወስምዓት ፤ ጸራ ፤
ወትእዛዛት ፤ አንስ እብለክሙ ፤
ወምሳሌያት ፤ ምሳሌ ዘርዕ ከነዚህ በቀር
ወፈቃደ ኵሎሙ ዘበውስቴታ ፩ እሙንቱ ፤

በሱዋ ያለ የሁሉ ፈቃድ አንድ ነው ። አንድም ፈቂድ ዘበውስቴታ በሱዋ ያለውን በመሻት ሁሉ አንድ ናቸው ።

ኍልቌ አርእስት ነገራት ዘ፬ቱ ወንጌላት ሰባክያን በዘናመጽእ በክፉለ ምዕራፋተ ኃይለ ቃል ፤
የአራቱን ወንጌል የዓቢይ ምዕራፍ ቍጥር የነገሩን ምስጢር ምዕራፍ በመክፈል ጊዜ በምናመጣው አለ ። አንድም ክፍለን ክፍለን በምናመጣው አለ ።
ወኵሉ ነገር እምኔሆን ውስተ ቀዳሚሃ

ዓቢይ ምዕራፍ በመጀመሪያው ነው ያውም በሚመጣው ነው ፤ ንኡስ ምዕራፍ ቀጥሎ በሚመጣው ነው ለሁለቱ ሁሉ ፤
ብያኔ ሮማዊ ፪፻፲ወ፱ አርእስት ፤
ሮማዊ ቍጥር ሮማዊ አቈጣጠር ሁለት መቶ ዐሥራ ዘጠን አርእስት ነው ፤
ማቴዎስ ፷ወ፰ አርእስት ፤
ማቴዎስ ስሳ ስምንት አርእስት ነው ፤
ማርቆስ ፵ወ፰ አርእስት ፤
ማርቆስ አርባ ስምንት አርእስት ነው ፤ ስሳና አርባ መቶ ስምንትና ስምንት ዐሥራ ስድስት ነው ፤ ዐሥራ ስድስትን ይዘህ ሂድ ።
ሉቃስ ፹ወ፫ አርእስት ።
ሉቃስ ሰማንያ ሦስት አርእስት ነው ፤ አሥራ ስድስትና ሦስት ዐሥራ ዘጠኝ ።
ዮሐንስ ፳ አርእስት ።

ዮሐንስ ሃያ አርእስት ነው ። ሃያን ከሰማን ያላይ ብትደርበው መቶ ይሆናል ። ሁለት መቶ ዐሥራ ዘጠኝ ያለው ይህ ነው ።

ጉልቄ አርእስት ንኡሳን እንተ ተሠርዓ አቅማር እንበይነ ዚአሃ ዘአንበርዋ አበው ቅዱሳን አሞንዮስ ወአውሳብዮስ በረከተ ጸሎቶሙ የሃሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ልመናቸው ክብራቸው ይደርብንና አበው ቅዱሳን ሐዋርያት የተናገሯት አሞንዮስ አውሳብዮስ የጸፏት ሰሌዳ ሰንጠረዥ የተጻፈላት ፣ እንድም አበው ቅዱሳን አሞንዮስ አውሳብዮስ አድርግ ፣ አበው ቅዱሳን አሞንዮስ አውሳብዮስ የጸፏት ሰሌዳ የጻፉላት ሰንጠረዥ የተጻፈላት የንኡስ ምዕራፍ ቍጥር

፲፻ ወ፩፻ ፷ ወ፭ አርእስት ፤ ሺህ መቶ ስሳ አምስት ነው ።

ማቴዎስ ፫፻ ፶ ወ፭ አርእስት ፤

ማቴዎስ ሦስት መቶ አምሳ አምስት ነው ። አምስት ባለው ስድስት ይላል ከውስጥ አግብቶ ሲዘራው አምስት ያለ እንደሆነ አንድ ወገን አድርጎ ስድስት ያለ እንደሆነ የመጨረሻውን ምዕራፍ ከሁለት ከፍሎ ነው ።

ማርቆስ ፪፻ ፴ ወ፮ አርእስት ፤

ማርቆስ ሁለት መቶ ሠላሳ ስድስት አርእስት ነው **ሦስት መቶና** ሁለት መቶ አምስት መቶ ፣ አምሳ **ሠላሳና ሰማንያ አምስትና** ስድስት ዐሥራ አንድ ።

ሉቃስ ፫፻ ፵ ወ፪ አርእስት ፤

ሉቃስ ሦስት መቶ አርባ ሁለት አርእስት ነው ። **አምስት መቶና ሦስት መቶ** ስምንት መቶ ከአርባው **ዐሥሩን ነሥተሽ ከዘጠና ላይ** ስትደርበው መቶ **ይሆናል ። ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ሦስት ቢል ።**

ዮሐንስ ፪፻ ፴ ወ፪ አርእስት ።

ዮሐንስ ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት አርእስት ነው ፤ ሺህ ከመቶ ይጎድል ሠላሳና ሠላሳው ስሳ ነው ፣ **ሁለትና ሦስት አምስት** ነው **መላው ሺህ ሦስት መቶ ስሳ አምስት** ነው ።

ወጉልቄ ምዕራፋት ዓበይት በመጽሐፈ ቅብጥ ፣ የዓቢይ ምዕራፍ ቍጥር በቅብጥ አቈጣጠር ። ሐተታ ቋንቋው ቅብጥ ነውና በመጽሐፈ ቅብጥ አለ ፣ እኛ ድም የገ የጸ ጸያፍ አለባቸውና ግብጽ ሲሉ ቅብጥ ይላሉ ፤ በግብጻውያን አቈጣጠር ።

፪፻ ፹ ወ፮ ምዕራፍ ።

ሁለት መቶ ሰማንያ ስድስት ምዕራፍ ነው ።
ማቴዎስ ፻ ወ ፩ ምዕራፍ ፣
ማቴዎስ መቶ አንድ ምዕራፍ ነው ፣
ማርቆስ ፶ ወ ፬ ምዕራፍ ፣
ማርቆስ አምሳ አራት ምዕራፍ ነው ።
ሉቃስ ፹ ወ፮ ምዕራፍ ፣
ሉቃስ ሰማንያ ስድስት ምዕራፍ ነው ።
ዮሐንስ ፵ ወ ፭ ምዕራፍ ፣

ዮሐንስ አርባ አምስት ምዕራፍ ነው ፣ ሐተታ አንድና አራት አምስት አምስትና አምስት ዐሥር ። አርባና አምሳ ዘጠና ፣ ዐሥሩን ከዘጠና ብትደርበው መቶ ይሆናል ። ሉቃስ እዳለው ። ሁለት መቶ ሰማንያ ስድስት ያለው ይህ ነው ።

ወሶበ እንከ ዘከርነ በእምግንነ ዘበጽሐት ኀቤሁ ክሂል እምአሕጽሮ ውስተ መጽሐፍ እስትጕቡዕ ጓቱ እንተ አቀደምናሃ ቀዲሙ ንቅትለኬኒያሃበከመ ሠርዑ አበው አሞንዮስ ወአውሳብዮስ እምአቅማራት በተሰጠችን አእምሯችን በደረሰችበት መጠን አስቀድመን በተናገርነው በስባቱ ክፍል የተሰበሰበውን በማሳጠር እሳጥረን ከተናገርን በኋላ ኪዚያ ኪያሐ አሞንዮስ አውሳብዮስ እንደጻፉ አሥሩን ቀመረ ፤ ሰንጠረዥ እንጻፍ ።

በዚህ መጽሐፍ ግን ንኡስ ምዕራፍ ፴፻ ፲፩ ነው ። ማለት ፣ ማቴዎስ ፻፷፪፤ ማርቆስ ፹፯ ፣ ሉቃስ ፻፴፭ ። ዮሐንስ ፳ ፤ ዓቢይ ምዕራፍ ደግሞ ፹፱ ነው ። ማለት ማቴዎስ ፳፰ ፣ ማርቆስ ፣ ፲፮ ። ሉቃስ ፳፬ ። ዮሐንስ ፳፩ ነው ።
በእንተ አኀብሮ ዘአርባዕቱ ወንጌላት ቅዱሳት ።
የአራቱ ወንጌላውያንን ነገር ለማስተባበር ።
ወረሰይዋ በማኀለቅት ።

ኅብዕ አርእስተ ነገር ያለው ሲፈጸም አደረጓት ።
በመትልወ ኀብረተ ቃሎሙ ።

የዘራቸውን አንድነት ቀጽሎ ቀጽሎ በመጻፍ አደረጉት ፤ ሐተታ በመጀመሪያው አራቱ የተባበሩበትን በሁለተኛው ሦስቱ በሦስተኛው ሦስቱ የተባበሩበትን ፲ቱ አቅማር ተጠየቀት ጥቃ ።
ዐሥሩ ሰንጠረዥ ታወቀ ተረዳ ።
ወሳቲ ፲፻ ፱ ወ፷ መስመር ።

ለቧም ስድስት መቶ አምሳ አምስት መስመር አሏት ፤ ሐተታ ን ሰ ምዕራፍ በዛ መስመር አነበሳ ቢሉ ንእስ ምዕራፍ እንደ ሰው እንደ እህል መስመር እንደ ቤት እንደ ውድማ ነው ፣ ባንድ ቤት ብዙ ሰው ባንድ ውድማ ብዙ እህል እንዲኖር ። ባንድ መስመርም ብዙ የንኡስ ምዕራፍ አኃዝ ይጻፋልና አምስት ባለው በዘጠነኛው ሰንጠረዥ ዐሥራ ዘጠኝ ይላል ፤ ይህን ዘጠኝ ያለ እንደሆነ ዘጠነኛውን ሀያ ይላል ።

ቀመር ቀዳማዊ ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ወዮሐንስ ፳ ወ፪ መስመር ።

አራቱ የተባበሩበት መጀመሪያው ሰንጠረዥ ስሳ ሁለት መስመር ነው እንዲህ እያልህ ሂድ ።

ቀመር ዳግማዊ ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ፻፲ወ፪ መስመር ።
ሦስቱ የተባበሩበት ለሁለተኛው ሰንጠረዥ መቶ ዐሥራ ሁለት መስመር ነው ፤ መቶ ሰማንያ አራት ይሆናል ።
ቀመር ሣልስ ማቴዎስ ወሉቃስ ወዮሐንስ ፳ ወ፩ መስመር ።
ሦስቱ የተባበሩበት ሦስተኛው ሰንጠረዥ ሃያ አንድ መስመር ነው ፣ ሃያውን ከሰማንያ ላይ ስትደርቢው መቶ ይሆናል ፤ አራትና አንድ አምስት ሁለት መቶ አምስት ።

ቀመር ራብዕ ማቴዎስ ወማርቆስ ወዮሐንስ ፳ ወ፮ መስመር ።

አራተኛው ሰንጠረዥ ሦስቱ የተባበሩት ሃያ ስድስት መስመር ነው ፤ አምስትና ስድስት ዐሥራ አንድ ሃያና ዐሥራ አንድ ሠላሳ አንድ ሁለት መቶ ሠላሳ አንድ ።

ቀመር ኃምስ ማቴዎስ ወሉቃስ ፹ ወ፫ መስመር ሁለቱ የተባበሩበት አምስተኛው ሰንጠረዥ ሰማንያ ሦስት መስመር ነው ፤ ሠላሳና ሰማንያ መቶ ዐሥር ሦስትና አንድ አራት ሦስት መቶ ዐሥራ አራት
ቀመር ሳድስ ማቴዎስ ወማርቆስ ፵ ወ፰ መስመር ሁለቱ የተባበሩበት ስድስተኛው ሰንጠረዥ አርባ ስምንት መስመር ነው ፤ ማርቆስና ሉቃስን አውጣ ሁሉንም እንዲህ እያልህ ሂድ ፤ ዐሥርና አርባ አምሳ አራትና ስምንት ዐሥራ ሁለት ። ሦስት መቶ ስሳ ሁለት ።

ቀመር ሳብዕ ማቴዎስ ወዮሐንስ ፯ መስመር ፡ ሁለቱ የተባበሩበት ሰባተኛው ሰንጠረዥ ሰባት መስመር ነው ፤ ሁለቱን ከሰባት ላይ ስትደርበው ዘጠኝ ይሆናል ሦስት መቶ ስሳ ዘጠኝ ማቴዎስ እስከ ሰባት ይዘምታል ከዚህ በታች የለውም ፤

ቀመር ሳምን ማርቆስ ወሉቃስ ፲ ወ፫ መስመር ፤ ሁለቱ የተባበሩበት ስምንተኛው ሰንጠረዥ ዐሥራ ሦስት መስመር ነው ሦስት መቶ ሰማንያ ሁለት ይሆናል ።

ቀመር ታስእ ሉቃስ ወዮሐንስ ፲ ወ፱ መስመር ሁለቱ የተባበሩበት ዘጠነኛው ሰንጠረዥ ዐሥራ ዘጠኝ መስመር ነው ፤ ሁለትን ካሥራ ዘጠኝ ላይ ቢደርቡት ሃያ አንድ ይሆናል ሃያውን ከሰማንያ ላይ ቢደርቡት መቶ ይሆናል ፤ አራት መቶ አንድ
ቀመር ዐሥር በዘተሌለዩ ቦቱ ኵሉ ለለአሐዱ አሐዱ እምሰባክያን ፪፻ ፶ ወ፬ መስመር ።
ከአራቱ ወንጌላውያን አንዱም አንዱ እያንዳንዱ የተባበሩበት ዐሥረኛው ሰንጠረዥ ሁለት መቶ አምሳ አራት መስመር ነው ። ማቴዎስ ፷ ወ፪ መስመር ማቴዎስ ስሳ ሁለት መስመር ነው ፤ ማርቆስ ፳ወ፩ መስመር ማርቆስ ሃያ አንድ መስመር ነው ስሳና ሀያ ሰማንያ አንድና ሁለት ሦስት ሰማንያ ሦስት ፤

ሉቃስ ፸ወ፪ መስመር ፤ ሉቃስ ሰባ ሁለት መስመር ነው ፤ ሰባና ሰማንያ ፡ መቶ አምሳ ፤ ሦስትና ሁለት አምስት ፤ መቶ አምሳ አምስት ፤ ዮሐንስ ፺ወ፱ መስመር ፡ ዮሐንስ ዘጠና ዘጠኝ መስመር ነው በዘጠኝ ላይ አምስትን የደረቡ እንደ ሆነ ዐሥራ አራት ይሆናል ። ዐሥራ አራትና ዘጠና መቶ አራት ሁለት መቶ አምሳ አራት ሆነ ፤ አራቱ የተባበሩበት አራት መቶ አንድ የተለያዩበት ሁለት መቶ አምሳ አራት መላው ስድስት መቶ አምሳ አምስት
ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማቴዎስ ቃሉ ፳፻ ወ፯፻ ማቴዎስ ያስተማረው የወንጌል ዘሩ ሁለት ሺህ ከሰባት መቶ ነው ።

ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማርቆስ ቃሉ ፲፻ ወ፯፻ ፤ ማርቆስ ያስተማረው የወንጌል ዘሩ ሺህ ከሰባት። መቶ ነው ፤ አራት ሺህ ከአራት መቶ ይሆናል ። ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ሉቃስ ቃሉ ፳፻ ወ፰፻ ሉቃስ ያስተማረው የወንጌል ዘሩ ሁለት ሺህ ከስምንት መቶ ነው ፤ ስምንት መቶና አራት መቶ ሺህ ከሁለት መቶ ይሆናል ፡ ሰባት ሺህ ከሁለት መቶ ወንጌል ቅዱስ ዘሰበከ ዮሐንስ ቃሉ ፳፻ ወ፯፻ ዮሐንስ ያስተማረው የወንጌል ዘሩ ሁለት ሽህ ከሰባት መቶ ነው ፤ ሰባት መቶና ሁለት መቶ ዘጠኝ መቶ ይሆናል ።

ወኮነ ድሙረ ቃሎሙ ለዓርባዕቱ ወንጌላት ፺፻ ወ፱፻ የአራቱ ወንጌላት የዘራቸው ቍጥር ድሙሩ ዘጠኝ ሽህ ከዘጠኝ መቶ ነው ።

ከመ ታእምሩ ኍልቍ ቃላቲሆሙ ለአርባዕቱ ወንጌላት ጸሐፍነ ለከሙ በጸጋሁ ለእግዚአብሔር የአራቱ ወንጌላውያን የዘራቸውን ቍጥር ታውቁ ዘንድ እግዚአብሔር ገልጾልን ጻፍንላችሁ ።

ወምንባረ ቃሎሙሰ ለ፬ቱ ወንጌላት ፺፻ ወ፬፻ ፵ ወ፱ አራቱ ወንጌላውያን በዘር የተባበሩበት ግን ዘጠኝ ሽህ ከአራት መቶ ዓርባ ዘጠኝ ነው ፤ የተለያዩበት አራት መቶ አምሳ አንድ ነው ።
ወከመዝ ኀብሩ አርባዕቲሆሙ ፤
አራቱ ወንጌላውን በዚህን ያህል ዘር ተባበሩ ። ዘብእሲ ማቴዎስ ፤

በገጸ ብእሲ የተመሰለ ማቴዎስ ፤
ዘአንበሳ ማርቆስ ፤
በገጸ አንበሣ የተመሰለ ማርቆስ
ዘላህም ሉቃስ ፤

በገጸ ላህም የተመሰለ ሉቃስ
ዘንስር ዮሐንስ ፡

በገጸ ንስር የተመሰለ ዮሐንስ ፤
ዘልዑለ ይሠርር ወልዑለ ይጸርሕ ወልዑለ ይሰብክ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም አሜን አካል ከህልውና ተገልጾለት ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ተሰጥቶት ቀዳሚሁ ቃል ብሎ የተናገረ ዮሐንስ ፡፡

ስምንተኛ ጉባኤ ፤

አልፈህ ግጻዌ ሥርዓት በል ፤ ታሪክ የመጻሕፍትን መልክ ከዚህ ይናገራሉ ፤ ታችኛው ግልየት ጎዳና ፤ ላይኛው ገጽ እርእስት ግልየት ጎዳና፣ ዳርና ዳሩ ገጽ ምስማክ ግልየት ጎዳና መካከሉ ዓምድ ሐውልት ግልየት ጎዳና ቀለም የመደቀበት መስመር መሰረ የሄደበት ሲራክ አራት ጥቁር አምስት ቀይ ነጥብ ሁለት ጥቁር ምስት ቀይ ስረዝ ሁለት ጥቁር ነጥብ ይባላል ፡፡ ግጻዌ ሥርዓት በአንተ ኅብረተ ቃላት የ፬ቱ ወንጌላት ፡፡
የአራቱ ወንጌላውያንን ነገር ለማስተባበር የአራቱ ወንጌላውያን የተገለጸ ሥርዓት ይህ ነው ያጌጸ ወደለዎ ለዮሐንስ ግጻዌ እንዲል ፡፡
እንዘ ይትሉ ረድኤተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ክልኤቱ ባሕቲቶሙ ጸሐፉ እንከ ወንጌለ እምሐዋርያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እየቃኛቸው እያገዛቸው ከሐዋርያት ሁለቱ ብቻ ወንጌልን ጻፉ ፡፡
ወክልኤቱ እመትሎሆሙ ፤

ሁለቱ ሐዋርያትን ተከትለው ከሚያስተምሩ ከሰባ አርድእት ወገን ናቸው ፡፡
አሐዱ ዘጳውሎስ ፤ አንዱ የጳውሎስ ደቀ መዝሙር ሉቃስ ነው ፤
ወአሐዱ ዘጴጥሮስ ረድአ ዚአሁ ፡፡

አንዱ የጴጥሮስ ደቀመዝሙር ማርቆስ ነው ፡፡
ምስለ ማቴዎስ ወዮሐንስ ጸሐፉ እንከ ወንጌላተ እንዘ ኢየኃሥሡ ክብረ ለርእሶሙ ፡፡
ለራሳቸው ክብር ሳይሹ እንበላበት እንጠጣበት እንኖርበት እንሸለምበታለን ሳይሉ ከማቴዎስ ከዮሐንስ ጋራ ጻፉ እነዚያ እንደጻፉ ጻፉ ፡፡
አላ በከመ ይትፈቀድ ፤

እንደሚወደድ አድርገው ንባቡን አጉልተው ምሥጢሩን አርቅቀው ጻፉ ሐተታ የፈላስፎች መጽሐፍ የሆን እንደሆነ ንባቡ ረቂቅ ጨጨጨ ፀፀፀ ሸሸሸ እያሉ ምሥጢር የለውም ፡፡
ወንጌልሰ ሶበ ተጽሕፈ አሐዱሂ እምአክለ ፤
ወንጌል ካራቱ አንዱ ቢጻፍ በበቃ ነበር ፡፡
ወየአክልሂ ፡፡

እስከ ዕለተ ምጽአት ለልጅ ልጅ ይበቃ ነበር ፡፡
ዳዕሙ አርባዕቲሆሙ ኃብሩ እለ ይጽሕፉ ፤
ወንጌልን የጻፉ አራቱ አንድ ሆኑ እንጂ ፤
ወኮኑ እንዘ ኢይትረአዩ ፤
ሳይተያዩ ጻፉ ፡፡
ወአኮ በ፩ዱ መካን ህልዎሙ ዘጸሐፉ ፤
ባንድ ቦታ ሁነው አልጻፉም ፤
ወኢሂ ተማከሩ ለአኀብሮ ቃላት ፡፡

ነገሩን ለማስተባበር አልተማከሩም ይህ እንዲህ ይሁን ይህን እንዲህ እንበለው ብለው ፤
ወእልቦ ኃሠሣ ማእከሎሙ ፡፡

በሳቸው ዘንድ መጠያየቅ የለምአልተጠያየቁምይህስ እምደምን ይሁን ይህንስ እንደምን እንበለው ብለው ዳዕሙ ከመ ዘአሐዱ አፍ ነበቡ ኵሎሙ ፡፡
እንዳንድ ልብ መካሪ እንዳንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው አንድ ነገር ተናገሩ እንጂ ፡፡
እሩየ ስብሐተ ወርእየተ ዘበአማን ዝንቱ ኮነ ፤
ተለያይተው የጻፉት ይህ ተያይተው እንደጻፉት ሁኖ ተገኘ ፡፡

ወሶበ ኢኮነ ከመዝ ጸላኢ ወኢመኑሂ እምኢአምነ ተለያይተው ጽፈዋት አንድ ሁና ባትገኝስ ማንም ማን መናፈቅ ወንጌል ደግ ሕግ እንደሆነች ባላመነም ነበር ፡፡

ወአኮ ድንቀተ ዘኮነ ዘመጠነዝ አኀብሮ ቃላት ፤
ድድቀተ ድድቀተ ይላል ይህን ያህል የነገር ማስተባበር የተደረገ በሐሰት በምትሐት አይደለም ፡፡
ወአምኵሉ ሐሜት ወትሕዝብተ ጸላዒ አድኃነት ፡፡
አራት ወገን ሁና ተጽፋ አንድ ሁና በመገኘቷከጠላት ጥርጥር ከጠላት ነቀፋ ራሷን አዳነች ሐተታ ወንጌል ተራ ሕግ ናት ብሎየጠረጠራት የነቀፋትየለምና ወፈድፋደ ያከብሮሙ ሰብእ በአንተ ዘጸሐፉ በብሩኅ ይልቁንምንባቡን አጉልተው ምሥጢሩን አርቅቀው ስለጻፉ ሰው ሁሉ ፈጽሞ ያከብራቸዋል ፡፡
ወጽሕፈቱስ ከመዝ ውእቱ ፤
ጽፈቱም ይህ ነው ፡፡
እስመ አምላክ ኮነ ሰብአ ፤
አምላክ ሰው ሆነ ብለው ነው ፡፡
ወበእንተ ትእምርታት ዘኮነ ፤
ድውይ ፈወሰ ብለው ነው ፡፡
ወመንክራተ ዘገብረ ፤
ጋኔን አወጣሙት አነሣ ብለው ነው ፡፡
ወበእንተ ዘተሰቅለ ወበእንተ ዘተቀብረ ፡፡
ተሰቀለ ተቀብረ ፡፡
ወበእንተ ትንሣኤሁ ወበእንተ ዕርገቱ ፡፡
ተነሣ ዓረገ ፡፡
ወበእንተ ምጽአቱ ፡፡
ዳግመኛ ይመጣል ብለው ነው ፡፡
እስመ ሀለዎ ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ፤
ሕያዋንን ሙታንን ይገዛ ዘንድ በሕያዋን በሙታን ይፈርድ ዘንድ አለውና ፡፡

ወከመ ዘወሀበ መድኃኒተ በምጽዋት ፤
አብ ቢሉ ልጁን እንደ ምጽዋት አድርጎ ሰጥቷል ወልድ ቢሉ አካሉን እንደ ምጽዋት አደርጎ ሰጥቷል አንድም ሥጋውን ደሙን እንደምጽዋት አድርጎ ሰጠ ብለው ነው ።

ወዘከመ ይቤ ኢያምጽእኩ ካልአ ሥርዓተ ዘይትቃወማ ለብሊት ሕግ ።

አስቀድማ የተሠራች ኦሪትን የምታሳልፍ ሕግን አልሰራሁም አለ ብለው ነው ። ኢይምበልከሙ ዘመጻእኩ አሰዐሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት አለ ብለው ነው ።

እስመ ወልድ ፍቁር ባሕቲቱ ብሑተ ልደተ ዘከመዝ ፤

በልደት ሥሉጥ የሚሆን ፍቁር ወልድ ብቻ ዛሬ ወንጌልን እንደሠራ ቀድሞም ኦሪትን የሠራ እሱ ነውና በእንተዝ ያለው ማንሻ ፤ አንድም በልደት ሥሉጥ የሚሆን ፍቁር ወልድ ብቻ ቀድሞ ኦሪትን እንደሠራ ዛሬም ወንጌልን የሚሠራ እሱ ነውና ።
ወበእንተዝ ኮነ ዘመጠነዝ አኀብሮ ቃላት ፤
ስለዚህ ይህን ያህል የነገር ማስተባበር ተደረገ ።
ሉቃስ ዝልፈተ አርአየ ፤

ሉቃስ አሌ ለከሙ አብዕልት እስመ ሠለጥከሙ ትፍሥሕተከሙ በዝንቱ ዓለም ብሎ ዘለፋን ተናገረ ።

ከመ ንትመራሕ ነገረ ርትዕ ጽንዕተ ፤
የማትፈርስ እውነተኛ ነገርን እናውቅ ዘንድ ፤
ወዮሐንስ አንሥአ ወከሐ እንዘ ይብል እምላዕሉ እፁኀበ አቡሁ ወረደ ።
እፁና እፁ አንድ ወገን ዮሐንስ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ወረደ እምሰማይ ብሎ ጽፎ የመናፍቃንን ክርክር ጸጥ አደረገ ።
እንዘ ክርስቶስ የሐወፆሙ ፤
ክርስቶስ እየቃኛቸው ዮሐንስ አንሥአ ወከሐ ሉቃስ ዝልፈተ አርአየ ፤
ወአፆካልዓኒሁ ውእቱ አንጎ ።
ከወንድሞቹ እብልጦ አካል ከህልውና ተገልጸላት ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ተሰጥቶት ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ተናገረ ።
ወማቴዎስኒ ዘእፆኢይሁድ ብዙኃነ አእመነ ፤
ማቴዎስም ከአይሁድ ወገን ብዙ ሰው አሳመነ ።
አንድም ከአይሁድ ወገን የሚሆን የጌታችን ልደት ለብዙ ሰው አስተማረ አንድም ከአይሁድ ወገን የሚሆን ማቴዎስም ብዙ አሳመነ ።
ወማርቆስኒ እንዘ ሀሎ ብሔረ ግብጽ አስተብቍዕዎ አርድእተ ዚአሁ ከመ ይግበር ከመዝ ፤
ማርቆስም በግብጽ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል ሥበቱ በደቀ መዛሙርቶቻቸው እንደጻፉ ጻፍልን ብለው ለመኑት ማለዱት ።
ወሉቃስኒ ካዕበ በሐዲስ ተናገረ ።
ዝልፈተ አርአየ ካለው ዳግመኛም ሉቃስ አብዝቶ ቆጸረ ።
ወእስከ አዳም አልዓለ ፤

እስከ አዳም ደረሰ ሐተታ ሌሎች የሚቈጥሩ እስከ ስድስት እስከ ሰባት ነው እንደሱ አብዝቶ የቈጠረ የለምና አንድም በሐዲስ ከነበረ ከዮሴፍ ጀምሮ በብሉይ እስከ ነበረ እስከ አዳም ደረሰ ወልደ ዮሴፍ ብሎ አዳም ወልደ እግዚአብሔር እስከ ማለት ደረሰ ።
ወአኮ በእሐቲ ማዕዘንት ጽሒፎሙ ዘደፈኑ ፤
ጽፈው ባንድ ቦታ አልተውም ።

አላ በኵሉ ምድር ወበኵሉ ባሕር ሰፍሑ ስምዓተ ለኵሉ ሰብእ ።

ባራቱ ማዕዘን ላሉ ሁሉ ጻፉ እንጂ ።
ወእንዘ መቃርዓት ሀልው ይትነበብ ዝንቱ እስከ ዮም መናፍቃን ባሉ ወንጌል እስከ ዛሬ ድረስ ይነበባል ይተረጎማል ።
ወአልቦ ዘአዕቀፈ እምዘጽሑፍ ወኢመኑሂ ፤
ከተጻፈው ጽፈት ማንም ማን የነቀፈ የለም ፤
አንድም አላ በኵሉ ብለህ መልስ ። ባራቱ ማዕዘን ዞረው ወንጌልን ለሰው ሁሉ አስተማሩ እንጂ አይሁድ መናፍቃንም ሳሉ ሁልጊዜ ይህ መጽሐፍ ይነገራል ትምህርቱንም የነቀፈ የለም ።
እንዘ ታረትዕ ኃይለ አምላክ ከሃሊተ ኵሉ ።
ሁሉን ማድረግ የሚቻላት ኃይል አምላካዊት እያቀናናት ፤
ወፈደፉደ እምኵሉ ።
ይልቁንም ወንጌል ሰትጻፍ ፤
ወሶበ ኢኮነ ከመዝ እፎ መጽብሐዊ ወመገልብ እምጠቡ ከመዝ ፤

እንዲህ ባይሆን መጸብሐዊ ማቴዎስ መግለቦ ሠሪ ዮሐንስ እንደምን በተራቀቁ ነበር አንድም እፎ እምቢበ በል በውን በግብር ምክንያት ያሸሽ የነበረ መጸብሐዊ ማቴዎስ እንደምን በተራቀቀ ነበር ገለቦ ይላል ትግሬ ሸሽ ሲል ።
ወኢኮነ በምትሐት ወኢበሕልም ዘኮነ ዝ ለእለ በየዋሃት ወበሃይማኖት ያነብብዎ ወየአምኑ ፤
አምነው በሃይማኖት ባለመቃወም ጸንተው ለሚመለከቱት የተደረገ ይህ በሐሰት በምትሐት አይደለም ወአኮ በሕይወቶሙ ከመ ፤
ማመናቸውም በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ብቻ አይደለም ዓዲ መዊቶሙሂ ፤
ከሞቱም በኋላ ነው እንጂ ።
አኮ ለ፩ ወ፪ቱ ሰብእ ወኢለ፫ት ። የጻፉ ለመቶ ሀያ ቤተ ሰብእ ብቻ አይደለም ።

አሳ ለአህጉር ወለአሕዛብ ወለሕዝብ ወለምድር ወለባሕር ወለዓላዳስ ወለፀር ወለዙሉ ዓለም ።
ለሁሉም ነው እንጂ አንድም ለጥቂት ሰው ብቻ አይደለም በባሕር በየብስ በደሴት በሀገር ላሉ ለሕዝብም ለአሕዛብም ነው እንጂ ።
አእመኑ በዛንን ዘእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወውስተ መርሶ አብኡ ፤
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አጋዥነት አሳምነው ወደመንግሥተ ሰማያት ወደብ አገቡ ።
መጥዎ ኀብረተ ቃላት ቅዱሳት ዘ፬ቱ ወንጌላት ተፈጸመ ።
አራቱ ወንጌላውያን በዘር የተባበሩበትን ጽፎ መስጠት እለቀ ።
ወደ ኋላ ተመልሰህ አውሴብስ በል ፤
አውሴብስ ለቆጵርያኖስ ።

ታሪክ አሞንዮስ አውሳብዮስ ይህን ያህል ዓቢይ ምዕራፍ ይህን ያህል ንኡስ ምዕራፍ ይህን ያህል ዘር ብለው ጽፈው ከተለያዩ በኋላ ብልህ ደቀ መዝሙር የተለያዩበትን የተባበሩበትን ዘር ልወቅ ባለ ጊዜ እንደምን ይሆናል ባሕር ለባሕር ሲዋኝ ይኖራል ብሎ ይህን ሲሻ ቀኖና ገባ ባሥሩ ሰንጠረዥ አምሳል አሥር መሪ አኃዝ ተገልጾለት ይጽፋል ። አውሴብስ ለቆጵርያኖስ የላከው ክታብ ይህ ነው ። ዘአውሴብስ የአውሴብስ ክታብ ለቆጵሮያኖስ ትድረስለት እምአውሴብስ ይላል ። ከአውሴብስ የተላከች ክታብ ለቆጵርያኖስ ትድረስለት ፤ ቆጵርያኖስ ካህን ጨዋም ነው ይሉታል ።
ለዘእፌቅር ለእኁየ ፤
ለምወደው ለወንድሜ ለና ለ አንድ ወገን ።

ፍሥሐ ወሰላም ወዳኅና ለከ እምኀበ እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ዘንድ መንፈሳዊ ደስታ ይደረግልህ አሞንዮስ አስክንድራዊ በብዙኅ አስተሐምሞ ወጽሒቅ ገብረ ወኀደገ ለነ ዘቃለ ዘከመ ኃብሩ ፬ቱ ወንጌላውያን ወእምዝ አርአስተ ምንባባት ።

የእስክንድርያው ሰው አሞንዮስ በብዙ ትጋት በብዙ ጻሕቅ አራቱ ወንጌላውያን የተባበሩበትን የተለያዩበትን ፣ አንድም ሰንጠረዡን ቁራኛውን አንድም ዓቢይ ምዕራፉን ንኡስ ምዕራፉን ይህን አንድ ወገን ወእምዝ አርእስተ ምንባባት ዘሩን ጽፎ ተወልን፤ ሐተታ እሱ የሚጽፍ መሪ አኃዙን ነውና አንድ ሁነው የጻፉትን ለሱ ብቻ ለጥቶ ተናገረ ።

ወበአንተዝ እንከ መፍትው ጥንቶ ይትልው ።
ስለዚህ ማቴዎስን ሊመለከቱ ይገባል ።
ከመ ኢይኩን ሙሱነ ምንተኒ በተሲወ ንበቱ ።
በተመለከቱት ጊዜ አንድ በሚሆኑበት ዘር ልዩ እንዳይሆን ።
ወ፫ቱኒ ኢይትኀደጉ ፣
ሦስቱም እንዳይለያዩ ፣

ከመ እሙንቱኒ ይድኃኑ እምተጸርዖ በንበቱ ።
እሳቸውን በተመለከቷቸው ጊዜ ከመለየት ይድኑ ዘንድ ፍጹመ ሥጋ ወመለያልየ ይኩኑ ።

አንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ ቃል ተናጋሪ ይሆኑ ዘንድ እንጂ ፣ አንድም ፍጹም ሥጋ ወመለያልይ ፣ አካል ሕዋስ የተፈጸመለት ሰው ይሆኑ ዘንድ ነው እንጂ ።
ወተአምር ለለ፩ዱ ወንጌል መካነ ትእምርቱ ፣ አእምር ሲል ነው ። የያንዳንዱ ወንጌል የሰንጠረዡን ቦታ ዕወቅ ።
ወባሕቱ አማንን በዘሀልው እምጸማሁ ለቀዳማዊ ብእሲ ዘነገርን ለሞ ረከብኩ እነሂ ምክንያተ እንተ ከማሁ ቀመበል ሥርዓተ ወሐፈጥኩ ፲ተ ትእምርታተ ኀልዮ ወአንበርኩ ለከ ፤

አሞንዮስ እስክንድራዊ በብዙኅ አስተሐምሞ ወጽሒቀ ገብረ ወኀደገ ለነ ዘቃለ ዘከመ ኃብሩ ፬ቱ ወንጌላውያን ወአምዝ አርአስተ ምንባባት ብለን ስሙን ያነሣነው አሞንዮስ በጻፈበት በኩል እኔም በጾፈት እሷን የምትመስል እንደሷ ያለች አግኝቼ በዐሥር ሰንጠረዥ አምሳል ዐሥሩን መሪ አኃዝ ጽፌ ተውኩልህ ።
ወስመይከዎ ለቀዳማዊ አሐደ ።
ወሰመይኩ አሐደ ቀዳማዊ ይላል መጀመሪያውን ሰንጠረዥ አንድ አልሁት ።
ወአኀዝ ለቀዳማዊ ፣

የመጀመሪያውን ሰንጠረዥ መሪ አኀዝንም አንድ አልሁት ፤ ወአኀዝ ቀዳማዊ ወአኃዞ ለቀዳማዊ ይላል ወውእደ ኃብሩ አርባዕቲሆሙ ቃላተ ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ወዮሐንስ ፤
ወእደ ኃብሩ ይላል ፣ አራቱ በዘር ከተባበሩባት ዘንድ የተባበሩበትን ሰንጠረዥ አንድ አልሁት መሪ አኀዙንም አንድ አልሁት ።
ወውስተ ዳግም ፫ቱ ማቴዎስ ወማርቆስ ወሉቃስ ፣ በሁለተኛው ሰንጠረዥ ሦስቱ የተባበሩበትን ሁለተኛውን ሰንጠረዥ ሁለት አልሁት መሪውንም አኀዝ ሁለት አልሁት ፡ ወውስተ ሣልስ ሠለስቱ ማቴዎስ ወሉቃስ ወዮሐንስ ሦስቱ የተባበሩበትን ሦስተኛው ሰንጠረዥ ሦስት አልሁት መሪውንም አኀዝ ሦስት አልሁት ። ወውስተ ራብዕ ፫ቱ ማቴዎስ ወማርቆስ ወዮሐንስ ሦስቱ የተባበሩበትን አራተኛውን ሰንጠረዥ አራት አልሁት መሪውንም አኀዝ አራት አልሁት ።
ወውስተ ኃምስ ፪ቱ ማቴዎስ ወሉቃስ ።
ሁለቱ የተባበሩበትን አምስተኛውን ሰንጠረዥ አምስት አልሁት ። መሪውንም አኀዝ አምስት አልሁት ።
ወውስተ ሳድስ ፪ቱ ማቴዎስ ወማርቆስ ።
ሁለቱ የተባበሩበትን ስድስተኛውን ሰንጠረዥ ስድስት አልሁት መሪውንም አኀዝ ስድስት አልሁት ።
ወውስተ ሳብዕ ፪ቱ ማቴዎስ ወዮሐንስ ።

ሁለቱ የተባበሩብትን ሰባተኛውን ሰንጠረዥ ሰባት
አልሁት መሪውንም አኃዝ ሰባት አልሁት ።
ወውስተ ሳምን ፰ቱ ማርቆስ ዐሉቃስ ።
ሁለቱ የተባበሩትን ስምንተኛውን ሰንጠረዥ ስምንት
አልሁት መሪውንም አኃዝ ስምንት አልሁት
ወውስተ ታሥዕ ፱ ሉቃስ ወዮሐንስ ፤
ሁለቱ የተባበሩብትን ዘጠነኛውን ሰንጠረዥ ዘጠኝ
አልሁት መሪውንም አኃዝ ዘጠኝ አልሁት ፤
ወውስተ ዐሥር ዘዘዚአሆሙ በዐሥረኛው ሰንጠረዥ
አንዱም አንዱ እያንዳንዱ የተለያዩበትን ሰንጠረዥ
ዐሥር አልሁት መሪውንም አኃዝ ዐሥር አልሁት።
ወከመዝ ውእቱ ሥርዓቱ ዘተሠርዓ ።

አራቱ እንደ ተናገሩ እንደ ጻፉ የተጻፈው ጽፈት
ይህ ነው ።

ወነገሩ ስለእሐዱ ወንጌል በትልቁ አኃዙ ፤
የያንዳንዱ የወንጌል ዘሩ በንኡስ ምዕራፉ አኃዝ
ቍጥር ነው ፤ ወይቄጥን እም ቀዳማዊ መጽሐፈ ልደቱ
ሲል አንድ ይላል ፡ ወዳግም ወዙሉንኬ ሲል
ሁለት ይላል ። ወሣልሥ ለእግዚእነ ሲል ሦስት ይላል
እስከ ይትፈጸም መጽሐፉ እንዲህ እያለ
ማቴዎስ እስኪፈጸም ፤ አንድም መላው እስኪፈጸም
እንዲህ እያለ ይሄዳል ።

ወበ ትልቁ አኃዙ ቦቱ አኃዝ ዘበሲራኩ ዘያኤምር
ውስተ አይ ሥርዓተ ቀመር ሀሎ ።

የተባበሩበት የተለያዩበት ዘር በማናቸውም ሰንጠረዥ
ጽፈት እንዳለ የሚያስረዳ በየንኡስ ምዕራፍ
አኃዛቸው ቍጥር በሲራኩ የተጻፈ መሪ አኃዝ አስ
ወእምከመ አሐዱ ከመ ውእቱ ውስተ ቀዳማዊ ፤
መሪ አኃዙን አንድ ያለ እንደሆነ በመጀመሪያው
ሰንጠረዥ እንደሆነ ይታወቃል ።
ወእምከመ ክልኤቱ ። ከመ ውእቱ ውስተ ዳግማዊ
መሪ አኃዙን ሁለት ያለ እንደሆነ በሁለተኛው
ሰንጠረዥ እንደሆነ ይታወቃል ።
ወእምዝ እስከ ይትፌጸም ዐሠርቱ ሥርዓት ፤
ከዚህም በኋላ ዐሥሩ ሰንጠረዥ እስኪያልቅ መሪ
አኃዝ እንዲህ እያለ ይሄዳል ።
ወእምከመቦ ፤ አመ ከሠትከ እምአርባዕቱ ወንጌል
ካራቱ ወንጌል የሻኸው ኑሮህ ብትገልጽ ።
ወፈቀድከ ታእምር እለ መኑ እሙንቱ እለ ኃብሩ
ቃለ ተኃሥሥ ውስተ እቅማሪሁ ወትረከብ ።
በዘር የተባበሩ እነማንም እንደሆኑ ልታውቅ ብትወድ
ከሰንጠረዡ ገብተህ ፈልግ ታገኛለህ ፤
እእሚረከ አኃዘ ትልቁ ዘበሲራኩ ።
በሲራኩ የተጻፈ መሪ አኃዙን ዐውቀህ ፤
ወእሉሂ ውስቴቱ ።
እሳቸውም በሰንጠረዡ ተጽፈዋል ።
ከመ ውስተ ግልየቱ ትልቄ አኃዙ ለለአሐዱ ወንጌል
ዘዘዚአሆሙ ።
እየራስ እየራሳቸው እያንዳንዱ ወንጌል የመሪ አኃዛቸው
ቍጥር በግልየቱ እንደ ተጻፈ እሳቸውም
በሰንጠረዡ ተጽፈዋል ።
ወዘከመሂ ኃብሩ ቃለ ዘከመ ኃብሩ አርባዕቱ ወሠለስቱ
ወክልኤቱ ፤
አራቱ ሦስቱ ሁለቱ የተባበሩብትን እንደ ተባበሩ ።
ወአሐዱሂ ዘከመ ይቤሉ ፤
የተለያዩበትን እንደ ተለያዩ እንደ ተናገሩ ።
ወጸሐፍኩ ውስተ ቀዳማዊ ቀመር ዘከመ ኃብሩ
አርባዕቲሆሙ ።

አራቱ እንደ ተባበሩ በመጀመሪያው ሰንጠረዥ
ጽፌልሃለሁ ።

ውስተ ግልየቱ ለቀመር ትልቁ አኃዞሙ ለለአሐዱ
ወንጌል ።

በሰንጠረዥም የያንዳንዱ ወንጌል የመሪ አኃዛቸው
ቍጥር ተጽፏል ።

ወከማሁ ውስተ ወንጌልሂ ጽሑፍ ትልቄ አኃዙ ፥
ክማሁ ለማለት ነው የመሪ አኃዛቸውም ቍጥር በወንጌል
ተጽፏል ።

በዘየአምርዎ ኅበ ኃብሩ ፬ቱ በሲራከ አኃዙ ወውእደሂ ፫ቱ ወውእደሂ ፪ቱ ወ፩ዱሂ ።

በአኀዘ ሲራኩ ሲል ነው በሲራኩ የተጻፈውን መሪ
አኃዙን ዐውቀው አራቱ ሦስቱ ሁለቱ የተባበሩበትን
እንደ ተባበሩ ፥ ወ፩ሂ የተለያዩበትን እንደ ተለያዩ
፥ በሚያውቁት ገንዘብ ያውቁት ዘንድ ይሆን
የሚያውቁበት መሪ አኃዝ ጽፌልሃለሁ ።
ወእምከመ ረከቡ እንዘ ያነብቡ አኃዘ ዘበሲራኩ ።
ሲመለከቱ በሲራኩ የተጻፈውን መሪ አኃዙን ያገኙ
እንደሆነ ፥
ወፈቀዱ ያእምሩ አስማቲሆሙ ለእለ ኃብሩ ።
በዘር የተባበሩትን ስማቸውን ሊያውቁ ቢወዱ ፥
ይኅሥሡ ውስተ አቅማሪሁ ወይረከቡ ፤
ከሰንጠረዡ ገብተው ይፈልጉ ያገኛሉ ።
እስመ ውስቴቱ ጽሑፍ አስማቲሆሙ ።
ስማቸው ከውስጡ ተጽፏልና ።
ወጸሐፍኩ ዓዲ ትእምርተ ውስተ ወንጌል ትእምርተ
አኃዝ ዘበሲራኩ ።
ዳግመኛም በወንጌል የአንቀጽ ምልክት ጽፌያለሁ ፡
ኅበ ገብረ ተእምራተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት ካደረገበት
ጸጌትነቱን ሥራ ከሠራበት ዘንድ ፥ ሐተታ ሰንደቅ
አላማ ዙፋን መከዳ ድባብ ማሰሪ ይቀርጻል ።
ኅበሂ አዘዘ ወኅበሂ ገሠጸ ባሕረ ወኅበሂ መሐረ
ወኅበሂ ነበረ ።
ፃእ መንፈስ ርኩስ ብሎ ካዘዘበት ባሕርን ነፋሳትን
ከገሠጸበት ፥ ከተራራ ተቀምጦ ካስተማረበት ሳይ፥

ሐተታ ወምበር መቋሚያ መነሳንስ ድባብ ማሰሪ እንደ ጃንጥላቴ ዖፍ አድርጎ ይቀርጻል ።
ወትእምርት ኀበ እኃዙ ማዕተበ መስቀል ።

ነገረ መስቀልን ከሚያነሣሣበትቦታ የመስቀል ምል ክት አለ ፣ ሐተታ እንደተ አድርጎ ይቀርጻል ። ነገረ በቀልን ከሚያነሣበት እንደ እግረ ገመል አድርጎ ይቀርጻል ፤ ገመል በቀለኛ ናት አጥብቆ የመታትን እስከ ቢድስት እስከ ሰባትዓመትአትረሳውም ሰፍራ ሲመቻተ ገደል ገፍታ ትጥለዋለች ባጥብሳ ትረ ገጠጥለች ። ነቢያትን ከሚያነሣበት ጋ ጋ ጋ እያለ ይጽፋል ። ጋጋና ማለት ነው ። ጋ ጋ ኖ አስኪነጋ እየጮኹ እንዲያድር ነቢያትም ጌታ እስኪወለድ ትንቢት ተናግረዋልና ፣ እንድም ጋጋና ቀን ደጋ ወጥቶ ሲጮህ ይውላል ሌሊት ቆላ ወርዶ ያድራል። ነቢያትም ሲያል መውረድ አልቀረላቸውም በእደ እግዚአብሔር ተጠብቀዋል እንጂ ፣ ሐዋርያትን ከሚያነሣበት ጌ ጌ ጌ እያለ ይጽፋል ። ባለጌ ማለት ነው ። ባለጌ ባለርስት ነው ፤ ሐዋርያትምየመ ንግሥተ ሰማይ ባለቤቶች ናቸውና ፤ ይህንንም በነጭ በጥቁር በቀይ ይቀርጸዋል፤ ቀይ ደማቸውን ያፈሰሱና ጥቁር መከራቸው ጽኑዕ ነውና ፤ ነጭ ዋጋ አላቸውና ፍሥሐ ወሰላም ለነ በክርስቶስ ፣

በክርስቶስ የሚገኝ ፍቅር አንድነት ይደረግልን ፤ በስመ እግዚአብሐር መሐሪ ወመስተሣህል ስብሐ ሐት ለእግዚአብሐር ማዕርገ ወንጌል ወዝማሬ ዘበ አማን ።

ስብሐት ወዝማሬ ብለህ ግጠም ፣ወንጌልን ላከበረ ለእግዚአብሐር የባሕርይ ክብር ይገባዋልና ፣ መሐሪ መስተሣህል በሚሆን በእግዚአብሐር ስም አምነው ጸሐፍዋ ፬ቱ ወንጌላውያን አራቱ ወንጌላውያን ጻፉት በተአምራት ግሁዳት እምኀበ ኵሎሙ ሐዋርያት፣ በሐዋርያት ዘንድ በተገለጸ ተአምራት ።

ወመንክራት መዋኤ ኵሉ ሕሊናት ወቴክሥተ ቦቱ ጽድቅ ሃይማኖት ።

ሕሊናትን ድል የሚነሳ የሚያሳምን አንድነቱ ሦስ ትነቱ በተገለጸበት በተአምራት ወንጌልን ላከበረ፣
ወአስተኃፈረ ቦቱ ሰሕተተ ሰይጣናት ።
ኢተጥዓምን ኢትልክፍን ኢትግሥሥን ያሳለፈበት ወንጌልን ላከበረ ።
ወአፍለስ ፍጥረተ እግዚአብሐር ኀበ አምልኮቱ እምድኅረ አምልኮ ጣዖት ።

ሰውን ሁሉ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሐር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ በመለሰበት በተአምራት ወንጌልን ላከበረ ። አንድም የመለሰባት ወንጌልን ላከበረ ።
ወዪወወ ቦቱ ዪዋዌ ዘይወስድ ኀበ ሕይወት ዘለ ዓለም ።

ወደማያልፍ ሕይወት የሚያደርስ ምርኮኝነትን የማረከባት ወንጌልን በተአምራት ላከበረ ፣ አንድም ወደማያልፍ ሕይወት የሚያደርስ ምርኮኝነት የተማረ ኩባት ወንጌልን ላከበረ ፣ ሐተታ ለሞት የሚሆን የነ ብልጣሶር ምርኮ አለና እንዲህ አለ ።

ወአድኃነ ሰብአ እምከህደት ወእምተታልዎተ ፀር ወሞተ ኃጢአት ።

ሰውን ከክህደት ከሰይጣን ምርኮኝነት ቍራኝነት በኃጢአት ከሚመጣ ፍዳ ያዳነባት ወንጌልን በተ አምራት ላከበረ ።

ወፈጸመ ሕገ ርትዕ በሕገ ትሩፋት ፣
ኢትቅትል በኢታምጽእ ኢትዘሙን በዘርአይ ያሳለ ፈባት ወንጌልን ፣
ወሥርዓ ተፋቅሮ ፣

ተፋቀሩ በበይናቲክሙ የምትል ወንጌልን ወም ሕረተ ፤ ብፁዓን መሐርያን የምትል ወንጌልን ወኢሠንዮ ፤ ሠናየ ግበሩ ለኵሉ ያለባት ወንጌልን ወገዲፈ ጥሪት ።

እሰመ ትፈቅድ ትኩን ፍጹመ ሑር ወሢጥ ንዋየከ ያለባት ወንጌልን ፣

ወትሕትና ብፁዓን ትሑታን ያሰባት ወንጌልን ፣ ወንጽሐ ።

ብፁዓን ንጹሐነ ልብ ያለባት ወንጌልን በተአምራት ላከበረ ።

ወለዝንቱ መጽሐፍ ቅዱስ ዘያበርሃ ቦቱ ነፍሳት ከመ ከዋክብት ወጽጌያት ።

ነፍሳት እንደ ከዋክብት የሚያበሩባትንእንደጽጌያት የሚያሸበርቁባትን ወንጌልን ?

ወሰሊሁ ሕገ መድኃኒት ሰኵሉ ነፍሳት ፤
የድኅነት ሥራ የሚሆን ወንጌልን ፣
ወነቅዓ ሕይወት ለዘይትጌበሮ አምነ ኵሉ አንጋድ ከነገደ ካም ከነገደ ሴም ከነገደ ያፌት ተወልደው ለሚሠሩት የድኅነት መገኛ የሚሆን ወንጌልን ፤ ጸሐፍዋ ፬ቱ ወንጌላውያን ።
አራቱ ወንጌላውያን ጻፉት ።
በአህጉር ሊሉያን ፤

ቢቦታ ተለያይተው ጻፉት ፤ ሐተታ ማቴዎስ በፍል ስጥኤም ፣ ማርቆስ በግብጽ በሮምም ይላል ሉቃስ በመቄዶንያ ዮሐንስ በኤፌሶን ሁነው ጽፈዋል ። ወበአዝማን ውሉጣን ።

በዘመንም ተለያይተው ጻፉት ፤ ሐተታ ማቴዎስ ጌታ ባረገ ስምንት ተፈጽሞ ዘጠነኛው ሲጀመር ቀላ ውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ዘመን ማር ቆስ ፣ ጌታ ባረገ ዐሥራ አንድ ተፈጽሞ ዐሥራ ሁለ

ተኛው ሲጀመር፤ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በአራተኛው ዘመን ፥ ሉቃስ ሀያ አንደኛው ተፈጽሞ ሀያ ሁለተኛው ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ ባሥራ አራተኛው ዘመን ፥ ዮሐንስ ጌታ ባረገ በ፴ በ፴ አምስትም ይላል ። ኔሮን ቄሣር በነገሠ በሰባት ዓመት በስምንትም ይላል ፥ ሰባት ቢሉ ሲፈጸም ስምንት ቢሉ ሲጀመር ።

ወውእቶሙ ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ወዮሐንስ፤ አራት የተባሉም ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስ ዮሐንስ ናቸው ።

ወለማቴዎስ ስሙ ሌዊ ፥

የማቴዎስ ስሙ ሌዊ ነው ሌዊ ይባላል ።

ወትርጓሜሁ ኅሩይ ፥ ትርጓሜው ም ኅሩይ ይባላል ወውእቱ ዘእምነገደ ይሳኮር ዘእምሀገረ ናዝሬት ፤ ትውልዱ ነገዱ ከነገደ ይሳኮር ናዝሬት በሚባል አገር ነው ።

ስመ አቡሁ ዲቁ ፥ አባቱ ዲቁ ይባላል

ወስመ እሙ ካሩትያስ ፥ እናቱ ካሩትያስ ትባላለች

ወሶበ ተጋብኡ ኀቤሁ ጉባኤ ብዙኅ እምአይሁድ

ዘጸውኦሙ ወእለሂ አምኑ ወተጠምቁ ወኃሠሡ እምኔሁ ከመ ያስተጸንዕ አልባቢሆሙ ዘእአመኖሙ ቦቱ በቃል ወበመጽሐፍ ዘዜነዎሙ በልሳነ ዕብራይስጥ ወተሠጥወ ስእለቶሙ ።

ያስተማራቸው ያሳመናቸው ያጠመቃቸው ከይሁድ ወገን የሚሆኑ ብዙ ምእመናን ተሰብስበው በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳልና ብለው በቃል በዕብራይስጥ ያስተማራቸውን በመጽሐፍ ጽፎ ያስረዳቸው ዘንድ ጻፍልን ባሉት ጊዜ ልመናቸውን ተቀበላቸው ፤ በቃል ዘእአመኖሙ ቦቱ በልሳነ ዕብራይስጥ ያስተጸንዕ አልባቢሆሙ በመጽሐፍ ብለህ ግጠም ።

ወወጠነ ጽሒፈ ዝንቱ መጽሐፍ በፍልስጥኤም ወፈጸማ በሀንድ ዕብራይስጣዊ ።

በፍልስጥኤም ጀምሮ በህንድ ፈጸማት ፥

እመ ተሰዱ እርድእት እምድረ ይሁዳ በቀዳሚት ዓመት እመንግሥተ አቅሎንድዮስ ቄሣር ።

ምእመናን ከይሁዳ ወጥተው በሄዱ ጊዜ ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ዘመን አቅሎንድዮስ ቀላውዴዎስ ይለዋል ።

ወይእቲ በራብዕት ዓመት እምዓመተ ዕርገት ቅድስት ይችውም ጌታ ባረገ ስምንተኛው ተፈጽሞ ዘጠነኛው ሲጀመር ነው ።

ወኮነ ስምዓ በሀገረ ብስባሴ ውጉረ በእብን እመ ፲ቱ ወ፪ቱ ለጥቅምት ፥

በጥቅምት ባሥራ ሁለት ቀን ብስባራ በምትባል አገር በደንጊያ ተመትቶ በሰማዕትነት ሞተ ። ወተቀብረ በቅርጣግና ዘቄሣርያ ።

የቄሣርያ ክፍል ዕፃ በምትሆን በቅርጣግና ተቀበረ ወሰዛቲ ብሥራት ተርጐማ ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ በሀገረ እልእንሳን ።

የማቴዎስ ወንጌልን ዮሐንስ ወንጌላዊ በአልእንሳን አስተምሯታል ።

ወሰበከ ባቲ በህንድ ወበኢየሩሳሌም ፥

ኪያሃ ሲል ነው ፤ እሷን በህንድ በኢየሩሳሌም አስተማረ ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም አሜን ፥ እስጀምሮ ላስጨረሰን ለእግዚአብሔር ለዘላለሙ ክብር ይግባው ።

ብሥራተ ማቴዎስ ሐዋርያ ፩ዱ እም፲ ወ፪ቱ ሐዋርያት
ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስለ ፍቁሩ
ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ይህ ቃል የመለሰቱ ምእት ቃል ነው ጥንተ ነገሩ እንደምነው ቢሉ እግዚአብሔር አምቅድመ ዓለም በልብ የመከረውን በነቢያት ያናገረውን ለመፈጸም ሥጋ ሆነ ፡ ሥጋም ሁኖ ሕግ ጠባይዓዊን ሕግ መጽሐፋዊን ሲፈጽም አደገ ሕግ ጠባይዓዊ በየጥቂቱ ማደግ ነው ። ልህቀ በበሕቀ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ እንተ ይእቲ እሙ እንዲል ፤ ሕግ መጽሐፋዊ ሕገ ኦሪትን መፈጸም ነው ። እግዚእ ለኦሪት ገብረ በሕገ ኦሪት ከመ ይሣየጦሙ ለእለ ውስተ ኦሪት ወገብረ በሕገ ኦሪት እንዲል ፤ ሕገ ኦሪትን መፈጸም እንደምነው ቢሉ በ፰ ቀን ቤተ ግዝረት መግባት በ፵ ቀን ዕጓለ ርግብ ዘወገ ማዕነቅ ይዞ ከቤተ መቅደስ መግባት ካመተ ሦስተ ጊዜ ለገቢረ በዓል መውጣት ነው ። ፫ተ ጊዜያት ለለዓመተ ለያስተርኢ ተባዕትከ እንዲል ። በቀሩት ግን ከ፩ ዓመተ ዘታተ እንዳይወጡ ሥርዐተ ተሠርቶባቸዋል እሱ ግን አሥራ ሁለተ ዓመት ሲሆነው ወጥቷል ፡ መውጣቱ በማስተማር ነው እንጂ በሌላ አይደለምና ፡ እንዲህ ሲገዛ እያለ ፴ ዘመን ቢመላው በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ልጅነቱን አስመስክሮ ገዳም ሄደ ። ገዳም ኋይም ፵ መዓልት ፵ ሌሊተ ጾመ መዋዕለ ጾሙ ሲፈጸም ሰይጣን በ፫ ነገር ተፈታተነው ፡ ዘበስተ በተዐቢተ በፍቅረ ንዋይ በስስት ዘመጣበተ በትዕግሥተ በትዕቢት ዘመጣበተ በትሕትና በፍቅረ ንዋይ ዘመጣበት በአሊዓ ንዋይ ድል ነሣው ፡ ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ የሚያሰኙ እሊህ ናቸው ። ዛሬም በሊህ ድል ለነሣ ሰው የቀሩት ኃጣውእ አይቆሙለትም ። ከዚህ በኋላ ምድረ እሥራኤል ገብቶ ትምህርተ ታምራተ ጀመረ የአይን ታምራት አይተው የቃሉን ትምህርተ ሰምተው ካሥር አህጉር ከብዙ መንደር ተወጻጽተው ያምበተ ገዘፍ ያህል ሰዎች ተከተሉት ከሊህ መቶ ሃያ ቤተ ሰብአ ይመርጣል አበቀድሞ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያተ ። ወረሰየ እምሰብእ ዘአሁ ሐዋርያት እንዲል ፤ ቀጥሎ ሰባ ሁለቱን አርድእት ። አርአየ ወኃረየ ካልዓነ ሰብአ እንዲል ፤ ፸ም ይላል በአኃዝ ቀጥሎም ሠላሳ ስድስቱን ቅዱሳት አንስት መቶ ሃያ ቤተ ሰብ የሚያሰኙ እሊህ ናቸው ፡ በሊህ ትምህርት አይከፈልባቸውም ካደረበት ያድራሉና ። የቀሩት ግን ሲማሩ እየዋሉ ምሽት ይከለክላቸው ነበር ። ሳሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል በየፃቸው እየገባ ወር ወር ይሰብከላቸው ነበር ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተምሮ ትምህርቱ በምር ሲረዳለት ለመድኃኒተ ዓለም በቀራንዮ ተሰቀለ ወገብረ መድኃኒተ በማእከለ ምድር ኢይደልዎ ለነቢይ መዊት በአፍአ ዘእንበለ በኢየሩሳሌም እንዲል ፤ ተሰቅሎም በሞቱ ዓለምን አድኖ ፫ መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ተነሣ ። እበመ ውእቱ ቀሰፈነ ወይፌውሰነ ውእቱ አቍሰለነ ወይሜርየነ ወያሐይወነ በሰኑይ መዋዕል ፤ ወአመ ሣልስት ዕለት ንትነሣእ ። ወአመ ሣልስት ዕለት ሦጣ ለነፍስ ውስተ ሥጋሁ እንዲል ፤ ተነሥቶም መጽሐፈ ኪዳንን ፵ ቀን ለሐዋርያት አስተማረ ። ጉባኤ ሠርቶ ግን ያስተማራቸው ሦስት ቀን ነው ። የትንሣኤ የአግብኦተ ግብር የጥብርያዶስ ወዝንቱ ሣልሱ ለአግዚእነ እንዘ ያስተርእዮሙ ለአርዳኢሁ አምድኅረ ተንሥአ እሙታን እንዲል ። በበዛው መናገር ነው እንጂ ሳንዱም ለሁለቱም ለሦስቱም ባለሟሎቹ ሳይገለጽላቸው አይውልም አያድርም ነበር ፵ው ቀን ሲፈጸም አንተሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ብሎ አዟቸው ዓረገ ። ባረገ ባሥረኛው በተነሣ ባሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ሰደደላቸው ። አበበዚያ ወጾት ኑሮ ቢሉ ባሥረኛው መዓርግ የገዘን እና ነበርንና ከጥንተ ቦታተን እንደመለሰን ለማጠየቅ ። እንድም በዘጠኙ ከተማ ያሉ መላእክተ ሥጋዌውን ያላወቁ ነበሩና ለነዓ ቢያስተምር ይህማ እንዳይሆን ፈጣሪ ፍጡር ይመስል አንዱን ሥራውን ቢሠራ ባንዱ ይዘበበልበታል ወዲያስ ቢያስተምራቸው ወጾህሰ ቢሰዶባቸው ይማነውናል ብለው ሐተታ ከቀደመው ይገባል ። እንድም አሥሩን ቃላተ ፲ን ሕዋሳተ ጠብቁ ስጠ አተሁ እናንተም ብተጠብቁ ፡ ይሰጣችኋል በማለት ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ፍሩሃን የነበሩ ጥብዓን ሆኑ ። ከብልየት ታደሱ በአእምሮ ጐለመሱ ምሥጢር ተረጐሙ ፤ ፩ድ ቋንቋ ያውቁ የነበሩ ፸፩ ቋንቋ ተጨመረላቸው ፡ ዓመተ በኀበረተ መሢናቸው ኢየሩሳሌምን አስተማሩ ወነበሩ ዓመተ ፍጽምተ በኢየሩሳሌም እንዲል ። ከዚህ በኋላ ፡ ሐሩ ወመሐሩ ያላቸውን ነገር ያውቃሉና ዕፃ በዕፃ ተለው ይህነን ዓለም ተካፍለው ለማስተማር በሚወጹበት ጊዜ ምድረ ፍልስጥኤም ለማቴዎስ በዕፃ ደረሰው ፡ ከዚህ ገብቶ ጌታ ከፅንስ ጀምሮ ያደረገውን ታምራት ያስተማረውን ትምህርት የሠራውን ትሩፋት ቢነግራቸው እሥራኤል ናቸውና ከኦሪት ወደ ወንጌል ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ተመለሱ አመኑ ተጠመቁ ። ትምርት ካልደረሰበት ለማደረስ ወጥቶ በሚሄድበት ጊዜ በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳልና ጻፍልን ብለውት በዚህ

ምክንያት ይጽፋል ፤ አንድም እሱ እንደ አባትነቱ ከራሱ አንቅቶ ይጽፍላቸዋል ። አንድም በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ እስጢፋኖስን በደንጊያ ወግረው ከገደሉ በኋላ እስጢፋኖስ ነበር እንጂ ። ባፍና በመጣፍ የማይቻል የቀሩትንስ ሐዋርያት መበተን አይሳነንም ብለዋል ፡ ሐዋርያትም ይኸን ሰምተው እንክስ ንትመየጥ መንገለ አሕዛብ ብለዋል ፤ ያመኑት እኛ ሐዲሳን አትክልት ነን ካልጻፋችሁልን እንደምን ይሆናል ብለዋቸው በዚህ ምክንያት ይጽፋል አንድም ያላመኑት አይሁድ ያመኑትን ክርስቶስን ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም ነው ትሉ ታላችሁ እንጂ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም መሆኑን እስኪ ስፍራችሁ ቀጽራችሁ አስረክቡን ብለዋቸዋል ሳትወም በዕውቀተ ፍጹማን አይደሉምና ከማኅበር ግቡተ ማስረዳተ ሊባናችው ይልኩባታል ። ቦኬሃኬ ተንሥአ ማቴዎስ ዘመተንሥአተ ማይ ላዕለ እሳተ እንዲል ተናዶ ተነሥቶ በዚህ ምክንያት ይጽፋል አጻጻፉም ስለፈት ነገር ነው ክፍለ ዘመኑን ለመናገር ፤ በዘር ሰማኬ ተወለደ ብለውታልና ዘእንበለ ይትቃረቡ ተረክበት ፅንስተ እመንፈስ ቅዱስ ለማለተ ዮሐንስ የአብዮ ብለውታልና ዘኢይደልወኒ ፅጹር ቶታነ አሣዕኒሁ እምእገሪሁ ለማለት ፤ በብዔል ኬዞኡል ያወፅኦሙ ለአጋንንት ብለውታል በመንፈስ እግዚአብሔር ያወፅኦሙ ለአጋንንት ለማበት ፩ዱ እምነቢያት ብለውታልና እግዚእ ነቢያት እንደሆነ ለማጠየቅ ፤ መዋዕለ ጽሒፈት ማቴዎስ ጌታ ካረገ ስምንት ቢሉ ሲፈጸም ዘጠኝ ቢሉ ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ማርቆስ ጌታ ካረገ ዐሥራ አንድ ቢሉ ሲፈጸም ዐሥራ ሁለት ቢሉ ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ ባራተኛው ዐመተ ። ሉቃስ ጌታ ካረገ ሀያ አንደኛው ተፈጽሞ ሀያ ሁለተኛ ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ ባሥራ አራት ዓመተ ። ዮሐንስ ጌታ ካረገ በሠላሳ በሠላሳ አምስትም ይላል ኔሮን ቄሣር በነገሠ በሰባት ቢሉ ሲፈጸም በስምንት ቢሉ ሲጀመር ። ጸሐፍቱም ሁለቱ ከሐዋርያት ሁለቱ ከአርድእት ናቸው ። ሐዋርያት ጨርሰው እንዲጽፏት ያላደረገ ሁለቱን ከአርድዕት ያጻፈ ስለምን ቢሉ ስለ ክብረ አርድእት ። ጨርሰው ሐዋርያት ጽፈዋት ቢሆን አርድእት ለማስተማር በወጡ ጊዜ እነሆማ የአፍአ ሰዎች እንጂ ናቸው የውስጥማ ሰዎች ቢሆኑ ደጊቱን ሕገ ወንጌልን ባላጻፋቸውም ነበር ብለው አይሁድ ትምርታቸውን ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና ፡ ያውስ ቢሆን ጨርሰው አርድእት እንዲጽፏት ያላደረገ ሁለቱን ከሐዋርያት ያደረገ ስለምን ቢሉ ስለ ክብረ ወንጌል ፡ ጨርሰው አርድእት ጽፈዋት ቢሆን ይህችማ እንጂ ተርታ ሕግ ናት ። ደጊቱማ ሕግ ምሥጢረ ታምራትን በቤተ ኢያኤሮስ ምሥጢረ መንግሥትን በደብረ ታቦር ምሥጢረ ምጽአትን በደብረ ዘይት ምሥጢረ ጸሎትን በጌቴሴማኒ ባዩ አዕማደ ምድር በተባሉ በልበ ሐዋርያት እንጂ ቀርታለች እያሉ አይሁድ ደገኛይቱን ሕገ ወንጌልን ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና ፡ ያውስ ቢሆን ጸሐፍቱን ከፍ ብሎ አምስት ስድስት ዝቅ ብሎ ሁለት ሦስት ያላደረገ አራት ያደረገ ስለምን ቢሉ ጌታ ባራት በአራት ወገን የሠራው ብዙ ሥራ አለና በዚያ መስሎ ለመናገር በዚያውስ ላይ ሥርዓተ ምድር ተሠርዓ በሥርዓተ ሰማይ እንጂ ይባል ፡ በሰማይ አራት ጸወርተ መንበር ኪሩቤል አሉ ። ምነው ይጸውር ድደ ወይነብር ጠፈረ ሆኑ አንቀጸ ውስተ እጆሙ ለጽንፌ ዓለም በአራሁ እንዲል ። እሱ ይሸከሙታል እንጂ እሳቸው ይሸከሙታል ቢሉ ። በዘፈቀዱ የሚገለጽላቸው መንበሩን ተሸክመው የሚታዩ የሚቀድሱት በጸጋ የሚያድርባቸው ስለሆነ እንዲህ አለ እንጂ የሚሸከማቸውስ እሱ ነው ። እሊህም ገጸ ብእሲ ገጸ አንበሳ ገጸ ላህም ገጸ ንስር ናቸው ። ማቴዎስ በገጸ ብእሲ ይመሰላል ። ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም እያለ ሥጋዊ ልደቱን ይጽፋልና ማርቆስ በገጸ አንበሳ ይመሰላል አንበሳ ኑሮው ከሰው ርቆ በምድረ በዳ ነው ከዚያ ሆኖ ጣሕሩን ባሰማ ጊዜ አንስሳት ይገሠጹ ለራዊት ይደነግጣሉ ። ማርቆስም ከትምርተ ምድረ በዳ በምትሆን በግብጽ ቀዳሚሁ ለወንጌል እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ ባስተማረ ጊዜ ምእመናን ተገሥጸዋል አጋንንት መናፍቃን ደንግጸዋልና ፡ ዳግመኛም አንበሳ ለላህም ጌታው ነው ይሰብረዋል። እሱም ከግብጽ አምልኮተ ላህምን አጥፍቷልና ፡ ከትምርት ምድረ በዳነቷንም ከዚህ ይናገራል ፡

ቀድሞ ሙሴ አሮን ጒሳም አለ ኤርምያስ ወርደው ቢያስተምሯት አልተጠቀመችም ፍጹም ጥቅሟ በማርቆስ ነውና ፤ ሉቃስ በገጸ ላህም ይመሰላል ። አምጽኡ ላህመ መግዝዓ ወጥብሑ ንብላዕ ወንትፈሣሕ ምስሌሁ ዕያለ ምሳሌውን ይጽፋልና ዮሐንስ በገጸ ንስር ይመስላል ንስር በእግሩ ይሸከረከራል በክንፍ መጥቆ ይበራል በእግር እንዲያሽረክር እሱም እንደ ወንድሞቹ ወልደ እጓለ እመሕያው ወረደ እምሰማይ ብሎ ይጽፋል ። በክንፍ መጥቆ እንዲበር እሱም አካል ከሀልውና ተገልጸለት ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ተናግሯልና ። አንድም አንስር ዘኾመር በብርሃን አዕይንቲሁ እንዲል ፤ የንስር ዓይኑ ጽሩይ ነው ሽቅብ መጥቶ ረቦ ቁልቁል በተመለከተ ጊዜ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ሥጋ ብትሆን አትሰወረውም ያችን አንሥቶ ይመገባታል ። እሱም አካል ከሀልውና ተገልጾለት ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ተሰጥቶት ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ተና

ገሯልና አቃወማቸውንም ከዚህ ይናገራሉ ገጸ ብእሲ አቀዋወሙ በምሥራቅ ፊቱ ወደ ምዕራብ ። ገጸ አንበሳ አቀዋወሙ በምዕራብ ፊቱ ወደ ምሥራቅ ። ገጸ ላህም አቀዋወሙ በሰሜን ፊቱ ወደ ደቡብ ፡ ገጸ ንስር አቀዋወሙ በደቡብ ፊቱ ወደ ሰሜን ፡ ማቴዎስ ጽፎ ለማርቆስ ደቀ መዛሙርት ፡ ማርቆስ ጽፎ ለማቴዎስ ደቀ መዛሙርት ፡ ሉቃስ ጽፎ ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ዮሐንስ ጽፎ ለሉቃስ ደቀ መዛሙርት መስጠታቸውን መናገር ነው ። ወንጌል በጥንተ ስብከት የደረሰችበትን መናገር ነው እንጂ ኋላስ ከሁሉ ደርሳለች ። በ፬ቱ አፍላጋት ይመስላሉ ። እሊህ ከገነት ካንድ ከዕፀ ሕይወት ሥር ነቅተው ውኅነታቸውን ይህን ዓለም ዞረው አጠጥተው ዕፀዋትን ከይብስት ወደ ልምላሜ ከልምላሜ ወደ ጽጌ ከጽጌ ወደ ፍሬ ያደርሳሉ ። አራቱ ወንጌላውያንም ወንጌልን ካንድ ከጌታ ቀምረው ይህን ዓለም ዞረው አስተምረው ምእመናንን ከይብስተ ኃጢአት ወደ ልምላሜ ንስሐ ከልምላሜ ንስሐ ወደ ጽጌ ትሩፋት ከጽጌ ትሩፋት ወደ ፍሬ ክብር ያደርሳሉና ፤ እኒህም ኤፌሶን ግዮን ጤግሮስ ኤፍራጥስ ናቸው ። ኤፌሶን ፈለገ ሀሊብ ነው ። ርስትነቱም የሕፃናት ርስት ነው ማቴዎስ በዚህ ይመስላል ። ከመ ሀሊብ ሀለብክኒ ወከመ ግብት አርጋዕከኒ እንዲል ። በዘር የሚወለዱ የእሊሙን ልደት ይጽፋልና ፤ ዳግመኛ ሄሮድስ ያስፈጃቸውን የሕፃናትን ነገር ይናገራልና ፤ ግዮን ፈለገ ወይን ነው ርስትነቱም ቢጾሙ ቢሰልዩም ሥራቸውን ደስ ብሏቸው የሚሠሩ ሰዎች ርስት ነው ። ማርቆስ በዚህ ይመሰላል ። ወይን ያስተፌሥሕ ልበ ሰብእ እንጂ ይላል ወንጌሉን ሁሉን ደስ በሚያሰኝ በዕርገት ይጨርሳልና ። በዚህ ሁሉም ይተባበሩበታል ብሎ ቅብዓ ትፍሥሕት መንፈስ ቅዱስ በሚሰጥበት በጥምቀት ይጀምራልና ፤ ጤግሮስ ፈለገ ሙዓር ነው ርስትነቱም ጸዋሬ ነገር የሚቻላቸው ሰዎች ርስት ነው ። ሉቃስ በዚህ ይመስላል ። መዓር እንጂ ከቡድ ነው ። እሱም አባ ስረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ በትዕግሥትከሙ ታጠርይዎ ለነፍስከሙ እያለ ከቡድ ከቡድ ነገር ይጽፋልና ፤ ኤፍራጥስ ፈለገ ዘይት ነው፡ ርስትነቱም የሰማዕታት ርስት ነው ። ዮሐንስ በዚህ ይመሰላል ዘይት ጽኑዕ ነው ። እሱም ጽንዑ እስመ አነ ሞእክዎ ለዓለም እያለ ይጽፋልና ። ዘይት ብሩህ ነው የሰውን ልቡና በትምህርቱ ብሩህ ያደርጋልና ዳግመኛም ዘይት አራቱን ሽቱ ሰቦ በመዓዛ አንድ ያደርጋቸዋል ፤ እሱም ወንድሞቹን በምሥጢር ይበዘብዛቸዋልና ነቅዓቸውንም ከዚህ ይናገራሉ ፡ ቦ ዘይወፅእ እምሥራቅ ወየሐውር ለምዕራብ ከመ ይሰቂ ዘሀየ ። ቦ ዘይወፅእ እምዕራብ ወየሐውር ለምሥራቅ ከመ ይሰቂ ዘሀየ ፡ ቦ ዘይነቅዕ እምሰሜን ወይሠወጥ ለደቡብ ከመ ይሰቂ ዘሀየ ። ቦ ዘይነቅዕ እምደቡብ ወየሐውር ለሰሜን ከመ ይሰቂ ዘሀየ እንዲል ። ማቴዎስ ጽፎ ለማርቆስ ደቀ መዛሙርት ፡ ማርቆስ ጽፎ ለማቴዎስ ደቀ መዛሙርት ፡ ሉቃስ ጽፎ ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ፡ ዮሐንስ ጽፎ ለሉቃስ ደቀ መዛሙርት መስጠታቸውን ወንጌል በጥንተ ስብከት የደረሰችበትን መናገር ነው እንጂ ። ከዚህ በኋላስ ከሁሉ ደርሳለች ፡ በ፬ቱ ነፋሳተ ምሕረት ይመስላሉ ፡ ፬ቱ ነፋሳተ ምሕረት ፡ ለሰው ሕይወት ጽንዕ ይሆናል ፡ ሕይወት ለመሆናቸው እስመ ነፋሳት ነፍሳቲሆሙ ለማያት እስመ እምሁከተ ነፋሳት ንስሕቦ ለቁመተ ሥጋነ ፡ እስመ ነፋስ ያገዝፎ ለፍሬ እንዲል ጽንዕ ለመሆናቸው ወገብረ አዕማደ ሰማይ በነፋስ ። ወይዔምድ በነፋስ እሉ እሙንቱ እለ ይረብብዋ ለልዕልና ሰማይ ይላል ። እኒህም በነፈሱ ጊዜ ለሰው አምስት ነገር ይመጣለታል ፡ ጠል ዝናም ሕይወት በረከት ፈውስ ፡ አራቱ ወንጌላውያንም ባስተማሩ ጊዜ ለሰው አምስት ነገር ይገኛልና እንደ ጠል ትምህርት እንደ ዝናም ሥጋው ደሙ እንደ ሕይወት ሕይወት መንፈሳዊ እንደ በረከት በረከት መንፈሳዊ ፤ አንድም መሳውም በረከተ ኅብስትን ይጽፋሉና እንደ ፈውስ ፈውስ መንፈሳዊ አንድም ፈውስ ንስሐ ፬ቱ ነፋሳተ ምሕረት ያለሙትን የሚያጠፉ ያለመለሙትን የሚያደርቁ ፬ ነፋሳተ መዓት አሉ ። እሊህም በነፈሱ ጊዜ በሰው አምስት ነገር ይመጣል ፡ ይብሰት ሐሩር ድምሳሴ አንበጣ አናኩዕ ፬ቱ ነፋሳተ ምሕረት ያለመለሙትን የሚያደርቁ ያለሙትን የሚያጠፉ ፬ት ነፋሳተ መዓት እንዳሉ ። ፬ቱ ወንጌላውያንም ያስተማሩትን የሚያስክዱ ያለሙተ የሚያጠፉ ፤ ፬፡ ቤተ አይሁድ አሉ ። ኃጥአን መጸብሐን ፡ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ሰዱቃውያን ረበናት መገብተ ምኩራብ ሊቃነ ካህናት ሞላሕቅተ ሕዝብ ፤ አልመተ ዝዕላን የሚል አብነት ይገኛል መላሕቅተ ሕዝብ ማለት ነው እኒህ ባስተማሩ ጊዜ በሰው ፭ ነገር ይታዘዛል ። እንደ ይብሰት ይብሰተ አእምሮ እንደ ሐሩር መከራ እንደ ድምሳሴ ደጋግ ሰዎች በሥጋቸው ክፉ ሰዎች በነፍሳቸው የሚጎዱ ሁነዋል ። እንደ አንበጣ ዓላዊ ንጉሥ መናፍቅ ጳጳስ እንደ አናኩዕ ብዝኃ ሠራዊት ፤ ፬ቱ ነፋሳተ መዓት በ፬ቱ ነፋሳተ ምሕረት ተወስነው ተገተው እንዲኖሩ የ፬ቱ ቤተ አይሁድም ትምህርት በ፬ቱ ወንጌላውያን ትምህርት ተወስኖ ተገቶ ይኖራልና ባራቱ ባሕርያት ይመሰላሉ ካራቱ ባሕርያት የወጣ ፍጥረት የለም ከ፬ቱ ወንጌላውያንም ትምህርት የወጣ የለምና በ፬ቱ መዓዝነ ዓለም ይመሰላሉ ከ፬ቱ መዓዝነ ዓለም የወጣ ፍጥረት የለም ካራቱ ወንጌላውያንም ትምህርት የወጣ የለምና በ፬ቱ ከዋክብት ይመሰላሉ ሕልመልሚሌክ ምልክኤል ናርኤል ይባ

ለሉ ። እሊህ ዓመቱን ካራት ይከፍሉታል ዘጠና አንድ ቀን ከ፲፭ ኬክሮስ ፺፩ ቀን ፤ ካሥራ አምስት ኬክሮስ ይደርሳቸዋል ፀሐይን ተከትለው ሥጋዊ ምግብ ይመግባሉ አራቱ ወንጌላውያንም ዘመኑን ካራት ተካፍለው ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትለው መንፈሳዊ ምግብና ይመግባሉና ባራቱ ክፍለ ዘመን ይመስላሉ ፣ ጸደይ ከረምት መፀው ሐጋይ ናቸው ጸደይ ወርኃ ዘርዕ ፣ ነው ። ማቴዎስ በዚህ ይመስላል ምሳሌ ዘርእን ከሁሉ ይልቅ አምልቶ ፣ አስፍቶ አብዝቶ ጽፏልና ዳግመኛም ወርኃ መሬት ነው ። እሱም ምድራዊ ልደቱን ይጽፋልና ከረምት ወርኃ ማይ ነው ። ማርቆስ በዚህ ይመስላል ፣ እሱም በጥምቀት ይጀምራልና መፀው ወርኃ ነፋስ ነው ። ሉቃስ በዚህ ይመስላል በአምሳለ ነፋስ የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስን ነገር መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ እያለ ይጽፋልና ፣ ሐጋይ ወርኃ እሳት ነው ። ደረቅ ነው ዮሐንስ በዚህ ይመስላል መስተፃርር መስተቃርን የሌለበት ደረቅ ቃል ፤ ቀዳሚሁ ቃል እያለ ይጽፋልና ባ፬ቱ አንስተ ያዕቆብ ይመስላሉ ልያ ባላ ዘለፋ ራሔል ይባላሉ ። ማቴዎስ በልያ ይመስላል ። በመጀመሪያ እንደወለደች እሱም ከሁሉ አስቀድሞ ይጽፋልና ማርቆስ በባላ ዓመተ ራሔል ይመስላል ። ከልያ ቀጽላ እንደወለደች ከማቴዎስ ቀጽሎ ይጽፋልና ። እሷ እመቤቷን አህላ መስላ እንደወለደች እሱም ቀዳሚሁ በማለት ጌታው ዮሐንስን ይመስላልና ። ሉቃስ በዘለፋ ዓመተ ልያ ይመስላል ከባላ ቀጽላ እንደወለደች ከማርቆስ ቀጽሎ ይጽፋልና ። እሱዋ እመቤቷን አኽላ መስላ እንደወለደች ምንም እሱ ሽቅብ እሱ ቁል ቁል ቢቆጥሩ ልደተ አበውን በመቍጠር ጌታው ማቴዎስን ይመስላልና ። ዮሐንስ በራሔል ይመስላል ከሁሉ በኋላ እንደወለደች ከሁሉ በኋላ ይጽፋልና ። እሱዋን ፍቅርት በኀበ ያዕቆብ ይላታል ። እሱንም ረድእ ዘያፈቅሮ ይለዋልና ፣ በ፬ ብሔረ ንግሥት በ፬ቱ ብሔረ ኦሪት ይመስላሉ ። ይህ ሁለት አራት ይሆናል እንዲህ ያለስ ብዙ አለ ብሎ ሙሴ አራት አድርጎ የጻፈውን ኃይለ ቃሉን አመጻጽቶ አንድ አድርጎ ጽፎ ዳግም ሕግ ብሎታል ። ወንጌልም አራት ሁና ተጽፋ አንድ ሕግ ለመባሏ ምሳሌ ነውና በ፬ እቀብተ ቤተመቅደስ ይመስላሉ ፩ት ፬ት ይሆናሉ እንዲህ ያለስ ብዙ አለ ብሎ ፬ት ፩ት ይሆናሉ ሁለቱ ከውስጥ ሁነው ተወካፍያን መባዕ ናቸው ፪ቱ በአፍአ ሁነው ኢይባዕ ሞዓባዊ ወአሞናዊ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ያለውን ይጠብቃሉ አራቱ ካምስቱ አራቱ ከስድስቱ አራቱ ከሰባቱ ቆመ ብእሲ ይሆናሉ ፣ እኒህ ካምስት ቦታ ሁነው የማይገባውን እንዳይገባ እንዲከለክሉ አራቱ ወንጌላውያንም ፬ቱን አእማደ ምሥጢር ፤ አስተምረው ከምእመናን ልቡና ክህደት ኑፋቄ እንዳይገባ ይከለክላሉና ፤ በ፬ መሠረታተ ቤተ መቅደስ ይመስላሉ ፥ ከታች ድልድሉ ሰባት ክንድ ነው በዚያው ላይ ባ፭ት ሰው ቁመት ልክ በዚያ ላይ በ፮ት ሰው ቁመት ልክ በዚያ ላይ በ፯ት ሰው ቁመት ልክ በዚያ ላይ ቤተ መቅደስ ታንጿል በቤተ መቅደስ ላይ ብርሃን ሰፍሮ ይታይ ነበር ። ፬ መሠረት ያ፬ቱ ወንጌላውያን ። መቅደስ የምእመናን ። ብርሃን የጌታ ምሳሌ ። ፬ቱ ወንጌላውያን ባስተማሯቸው በምእመናን ጌታ ለማደሩ ምሳሌ ። በ፬ቱ ገጸተ ኩሆሕ ባራቱ ገጸተ ታቦት ይመስላሉ ። ወንጌል ለሆሣዕና ባራት መዓዝን ትነበባለችና ይህስ ሁሉ መዓዝነ ዓለም ካለው ይገባል ብሎ ወንጌል መሠራቷ ስለ አራት ነገር ነውና ። ለጥምቀት ለተክሊል ለፍታት ለቍርባን ። መዋዕለ ጽሕፈት ተናግረናል ። አገርም ማቴዎስ በፍልስጥኤም ጀምሮ በህንድ ጨርሱዋል ። ወፈጸማ በህንድ እንዲል ። ማርቆስ በግብጽ በሮምም ይላል ። ሉቃስ በመቄዶንያ ዮሐንስ በኤፌሶን ። ልሳንም ማቴዎስ በዕብራይስጥ ማርቆስ በሮማይስጥ ሉቃስና ዮሐንስ በዮናኒ ። ዮሐንስን ለይቶ በፅርእ ይላል እንደ በቅላ እንደ ሐማሚን ጥቂት ጥቂት የልሳን መለያየት ነው፣ ወንጌልሂ ሶበ ተጽሕፈ ፩ዱ እምእክለ ወየአክልሂ ይላል ፣ ወንጌል ካራቱ አንዱ ቢጽፍ በበቃ ነበር ለልጅ ልጅም ይበቃ ነበር ይህስ እንዳይሆን ካንዱ የሌለው ካንዱ አለ ፣ ካንዱ ያለው ካንዱ የለም ብሎ ሶበ ተጽሕፈ ፩ዱ ። አራቱ አንድ ሁኖ ቢጽፍ በበቃ ነበር ፣ ለልጅ ልጅም ይበቃ ነበር ቦታ አንድ ሳያደርጋቸው ዘመን ሳያገናኛቸው ቋንቋ ሳያገጣጥማቸው አራት አድርገው ጽፈውት አንድ ሁኖ ቢገኝ የእግዚአብሔር ነገሩ የመንፈስ ቅዱስ ምሥጢሩ እንደሆነ ሊታወቅ አራት አድርገው ጽፈውታል እንጂ ሶበ ተጽሕፈ ፩ዱ እም እክለ ወየአክልሂ ፤ ከዚህም ሥጋዊ ምግብናን ከሦስት እንደከፈለ መንፈሳዊ ምግብና ከሦስት ከፈለ ሰው ከተወለደ ጀምሮ እስከ ሃያ ዓመት ያለው ምግበ ነፋስ ነው ብር ብር እያለ የሚሠራውን አያውቅም ። ወኢይክል ያእምር ዘውስተ ነፍሱ እንዲል ። ከሃያ እስከአርባ ያለው ዘመን ምግበ እሳት ነው ማወቁን ያውቀዋል እየተናደደ ይሠራዋል ። ከአርባ እስከ ስሳ ያለው ምግበ ማይ ነው ሰውነቱ እየደከመ ይሄዳል ፣ ተመልሶ የሕፃንነቱን ሥራ ልሥራ ቢል አይቻለውም ከተወለደ እስከ ሃያ ዘመን ያለው ከአዳም እስከ ሙሴ ያለው ዘመን አበው ነው ። የሚሠራውንም ሥራውን እንዳያውቀው ጽድቅና ኃጢአት ተለይቶ አይታወቅም ነበር ምንም እነ ሄኖክ እነ ኢዮብ አንድ አንድ ሰዎች ቢያውቁት ፣ ዛሬ ከቤተ መንግሥት የተመከረውን ምክር ሁለት ሦስት ባለሟሎች ቢያውቁት እንጂ

ሙሉ እንዲያመተው ፤ ከሃያ እስከ አርባ ያለው ዘመን አራት ነው ፤ እየተናደደ ዐውቆ እንዲሠራው ዐራትም ጽድቅና ኃጢአት ተለይቶ ታውቋል። ሙሉ እልክ እየገባ የሚሠራው ሁኑዋልና ፤ ወኃየሰ ገቡ ሕገ ኃጢአት ዘውስተ አባልየ ወፄወወኒ መንገሌው እንዲል ካርባ እስከ ስሳ ያለው ዘመን ወገል ነው ፤ ስውነቱ እየደከመ እንዲሄድ ኃጢአት ወፍቷል ። ወደክመ ሕጉ ለኃጢአት እንዲል ተመልሶ የሔዋንነቱን ሥራ ልሥራ ቢል እንዳይቻለው ወንጌልንም ሊለውጣት የተቻለው የለምና ። ይኸን አርእስት ፫ ፻ ሰጥተዋል በምን ምክንያት ቢሉ ዲዮቅልጥያኖስ መክስምያኖስ የሚባሉ ሁለት ዓላውያን ነገሥታት ተነሥተው አብያተ ጣዖታት ይትረኃዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትዓፀዋ ብለው ዐዋጅ ነገሩ ። አብያተ ክርስቲያናት ተተኩሱ መጻሕፍት ፈለሱ ። ከምእመናንም ወገን የሚሞቱት ሞቱ የሚፈልሱትም ተሰደዱ ። ዘመኑም አርባ ዘመን ነው [illegible] የሰማዕ ዘመን ሰማዕታት ብለው [illegible] እግዚአብሔር መፍቀሬ ሃይማኖት ርትዕ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስን እነመሳቸው መንግሥት ዐዋጅ መለሰው አብያተ ክርስቲያናት ይትረኃዋ አብያተ ጣዖታት ይትዓፀዋ ብሎ ፤ በዘመኑ አርዮስ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ ብሎ ተነሣ ። በዚህ ምክንያት ጉባኤ በኒቅያ ይሁን ብሎ ዐዋጅ ነገረ። ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንት ተሰብስበው አርዮስን አውግዘው ለይተው ሃይማኖት መልሰው እጽንተው በሚለያዩበት ጊዜ ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት ሰጥተዋል ። መልእክተ ያዕቆብ መልእክተ ጴጥሮስ መልእክተ ዮሐንስ መልእክተ ይሁዳ መልእክተ ጳውሎስ ፤ ብሥራተ ማቴዎስ ብሥራተ ማርቆስ ብሥራተ ሉቃስ ብሥራተ እብ ፤ ትሩፍ ረድእ ተናጋሪ በመለኮት ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ፍቁረ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ብለው ስለምን ቢሉ የጻሐፊው ደግነት የታወቀ እንደሆነ የመጽሐፉም ፣ ደግነት ይታወቃል ብለው ይደልዎ ለዘያነብብ ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዓለ መጽሐፍ ወእምዝ ያንብብ ወይምሀር እንዲል ። ወንጌል ብሥራት ስብከት ቢል አንድ ነው ፣ ወንጌል ብሂል በልሳነ ጽርእ ወትርጓሜሁ ስብከት እንዲል ፣ ዲያብሎስ እንደተሻረ ወልደ እግዚአብሔር እንደነገሠ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደጠፋ ትናገራለችና ልመናው ክብሩ ይደርብንና ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ማቴዎስ የጻፈው ወንጌል ይህ ነው።።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል
ቅዱስ ማቴዎስ እንደ ጻፈው ።

ምዕራፍ ፩ ።

፩ መጽሐፈ ልደቱ ለእግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ ።

ወንጌላውያን ሲጽፉ ራሳቸውን መሠረት አያደርጉም ሌሎች ግን ራሳቸውን መሠረት ያደርጋሉ ምንም የሚገልጽላቸው መንፈስ ቅዱስ ቢሆን የሚጽፉ ከራሳቸው አንቅተው ነውና ዳግመኛ ካንድ አገር ሁነው ጽፈው ወደ እንዱ አገር ይሰዱታልና ። ወንጌላውያን ግን የሚጽፉ ጌታ የተናገረውን ነው እንጂ ከራሳቸው አንቅተው አይደለምና በመካከል ሁነው ይጽፋሉና ፤ ዳግመኛ ምንም አንዱም አንዱ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ ቢል ነገር ለማያያዝ ነው ።

፩ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ቍጥር ይህ ነው ። ጸሐፈዮ ለብእሲ ከመ ዘሞተ መበ ውእቱ መዋዕል ወፅአ ትእዛዝ እምኀበ አውግስጦስ ቄሣር ከመ ይጸሐፍ ኵሉ ዓለም እንዲል ፡ እንድም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ወግ ታሪክ ይህ ነው፤ ስማ ለዳቤር ትካት ሀገረ መጽሐፍ እንዲል ፡ የወግ የታሪክ ሀገር ሲል ፡ ወግ የነትእማርን የነራኬብን የሩትን ያመጣል ። ታሪክ ወለእግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመዝ ውእቱ ልደቱ ብሎ ያመጣል ፡ ልደቱ ለእግዚእን አለ ፡ ብዙ ልደታት አሉና ከዚያ ሲለይ ፡ ልደተ አዳም እምድር ልደተ ሔዋን እምገቦ ። ልደተ አቤል እምከርሥ ልደተ በግዕ እምዕፅ ፡ ልደተ ሙታን እመቃብር አለ። እኒያ አውጭ ይሻሉ ። እሱ ግን በገዛ ሥልጣኑ ነውና ፡ የልደቱን ነገር ብቻ ይናገራልና መጽሐፈ ልደቱ አለ ምነው ቢሉ ፡ መጽሐፍ ባንድ መጀመር ኋላ ብዙ ማምጣት ልማድ ነው ። ከዚያ ሁሉ ኦሪት ዘልደት ይላል። የሥነ ፍጥረትን ብቻ ተናግሮ ይቀራልን መጽሐፈ ልደቱ ባለው በጥቂር አንድ ይላል የንኡስ ምዕራፍ አኃዝ ነው ፤ ማቴዎስ መጽሐፈ ልደቱ ማርቆስ አንተ ውእቱ ወልድየ ፡ ሉቃስ ወይመስሎሙ ወልደ ዮሴፍ ዮሐንስ ቀዳሚሁ ቃል ያለውን ሁሉም የጌትነት ነገር ከሆነ ብሎ አራቱ የተባበሩበት ሲል ፩ዱ ይላል ፡ ፫ቱ ቢል ማርቆስን አውጥቶ ፡ በሦስተኛው ሰንጠረዥ ማርቆስ ስምና ፤ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም ሉቃስ ም ፫፡ ቍ ፴፩ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ከነገሥታት ዳዊት ከአበው አብርሃም ብቻ ይወልዱታልና እንዲህን አለ ቢሉ ፤ ትንቢት የተነገረ ለኒህ ነውና ፡ ትንቢትማ ከነገሥታት ለሰሎሞን አነ እከውኖ አባሁ ወውእቱ ይከውነኒ ወልድየ ተብሎ ፤ ከአበውም ለሴም ለይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ቤቱ ለሴም ተብሎ ተነግሮ የለም ቢሉ የሚበዛ የዚህ ነውና ፡ በሚበዛው ተናገረ ። እንድም ተስፋ ለተስፋ ሲያነጽር በዘርእ ይትባረኩ ፡ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ያለውንና ፤ እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ያለውን ተስፋ ለተስፋ ሲያነጻጽር ። እንድም ዳዊት ሥርወ መንግሥት ነው ። አብርሃምም ሥርወ ሃይማኖት ነውና ። እስመ አብርሃም ኮነ ሥርወ ሃይማኖትን ወሃይማኖቶሙ ለአይሁድ እንዲል ። የዳዊትን ሥርወ መንግሥትነት ኋላ ያመጻል፤ እንድም እግዚአብሔር ፈጣሪያቸውን ዳዊት ንጉሣቸውን ቢያነሣላቸው ይወዳሉና ወየኃሥሥዎ ለእግዚአብሔር አምላኮሙ ወለዳዊት ንጉሦሙ እንዲል ፤ ዳዊትንም ከመውደዳቸው የተነሣ የነገሠውን ሁሉ ዳዊት ይሉት ነበር ። ወሶበ ሰምዓ ዘንተ ዳዊት ደንገፀት ነፍሱ ወነፍሰ ኵሉ ሕዝቡ እንዲሰው አካዝን ፤ እንድም ያላመኑት ያመኑትን ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም መሆኑን ሰፍራችሁ ቈጥራችሁ አስረክቡን ብለዋቸው ነበርና ስለዚህ እንዲህ አለ ፤ ከፍለ ዘመንም ለመናገር ፤ በዚያውስ ላይ አብርሃም አይቀድምም ዳዊት አይከተልም ቢሉ ፤ አባቱን አያውቅ እያቱን ናፈቅ ይሉኛል ብሎ ለጌታም ከአብርሃም ዳዊት ይቀርበዋልና ። እንድም እርካብ ተረግጦ ወደ ኮር መውጣት ባዳራሽ ገብቶ ወደእልፍኝ ማለፍ እንዲመች ። ወልደ ዳዊት ብሎ ወልደ አብርሃም ሲሉ ይመቻልና ። እንድም ጌታን ወልደ ዳዊት ዳዊትን ወልደ አብርሃም አለው እንድም ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም ዋዌ የቀረው ነው ፡ እንድም የጌታ ጥቅል ስሙ ነው ፤ ዕውራን በሆሣዕና ተማሃለነ ወልደ ዳዊት እንዳሉ ። ወልደ አብርሃም ብሎ ለጌታ ቀጸለለት ፡ እንድም ይዞ ለመሄድ ይመቸኝ

ብሎ ይዞት የሚሄድ አብርሃምን ነውና ወደ ኋላ አደረገው ።

፪ አብርሃም ወለዶ ለይስሐቅ ፥

፪ አብርሃም ይስሐቅን ወለደው ።

ከአጋር የተወለደ እስማኤል ከኬጡራ የተወለዱ ፮ቱ ሕፃናት ያሉ አይደለምን ስለምን ይስሐቅን ለይቶ አነሣው ቢሉ ነቢይ የሆነ እንደሆነ ልደተ አበውን ጠንቅቆ ይቆጥራልና መላውን ያነሣል ። ወንጌላዊ ግን የሚሻ የጌታን ልደት ነውና ። የጌታም መወለድ ከይስሐቅ ነው እንጂ ከነዚያ አይደለምና ። እንድም ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ። ትንቢት እምይስሐቅ ይስመይ ለከ ዘርዕ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌ ይስሐቅ መሥዋዕት ሁኖ ቀርቧል ። ጌታም መሥዋዕት ሁኖ ይቀርባልና ወይስሐቅኒ ወለዶ ለያዕቆብ ፥ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ ። እነዚያስ ዕሰት እናት ባያገናኛቸው ነው እኒህማ ዕለት እናት አገናኝቷቸው አንድ ቀን ተፀንሰው አንድ ቀን የተወለዱት ኤሳውን ስለምን ለይቶ ተወው ቢሉ ። ነቢይ የሆነ እንደሆነ ልደተ አበውን ጠንቅቆ ይቆጥራልና መላውን ያነሣል ፥ ወንጌላዊ ግን የሚሻ የጌታን ልደት ነውና ። የጌታም መወለድ ከያዕቆብ ነው እንጂ ከኤሳው አይደለምና ። እንድም ፤ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ። ትንቢት ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ ወያአትት ኃጢአተ እምእሥራኤል ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም በጸውፆተ ሐዋርያት አብዝተው ያመጣሉ ከዚያው ከፍለው ይናገሩታል ። ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ተጣልቶ ወደ አጐቱ ወደ ላባ ሲሄድ ከምንጭ አጠገብ ደረሰ ። ውኃው ደንጊያ ተገጥሞ አባግዕ ከድንጊያው ስፍረው ኖሎት ተሰብስበው አገኘ ። ምነው ከፍታችሁ አታጠጧቸውም አላቸው። መላው ኖሎት እንጂ ካልተሰበሰቡ ከፍቶ ማጠጣት አይሆንልንም አሉት ። ውኃው ኩሬ ነው ጠላት ጥቂት ራሱን ሁኖ መጥቶ መርዝ እንዳይበጠብጥበት ለ፶ ለ፷ የሚከፈት ደንጊያ ገጥመው ይሄዳሉ ። እሱ ብቻውን ከፍቶ አጠጥቶላቸዋል ያዕቆብ የጌታ ። ደንጊያው የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ። ውኃው የጥምቀት ። አባግዕ የምዕመናን ኖሎት የነቢያት የካህናት ምሳሌ ። ወያዕቆብኒ ወለደ ይሁዳሃ ወአኃዊሁ ። ዘፍ ፥ ፳፩ ፥ ፫ ፥ ፳፭ ፥ ፳፭ ፳፱፥ ፴፭ ያዕቆብም ይሁዳን ወንድሞቹን ወለደ የይስሐቅን ልደት በተናገረ ጊዜ እለ እስማኤልን የያዕቆብን ልደት በተናገረ ጊዜ ኤሣውን አላነሣም ከዚህ አሁን ደርሶ ይሁዳሃ ወአኃዊሁ እስ ምነው ቢሉት ጌታ ካሥራ ሁለቱ ነገድ ይወለዳልና ፥ እንድም ነቢይ ቢሆን አባቶቻችንን ከቍጥር አይለያቸውም ነበር ወንጌላዊ ስለምን ለይቶ ተዋቸው ብለው አይሁድ ደገኞይቱን ሕገ ወንጌልን ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና እንድም ለምሳሌ ይመቸኝ ብሎ ካሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ያልተወለደ ምግድረ ርስትን አይወርስም ። ያሥራ ሁለቱ ሐዋርያትንም ትምህርት ያልተቀበለ መንግሥተ ሰማያትን አይወርስምና ያውስ ቢሆን ይሁዳን ለይቶ ማንሣቱ ስለምነው ቢሉ ቅንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም። ትንቢት ኢይጠፍዕ ምስፍና ወምልክና እምእባሉ ለይሁዳ እስከ አመ ይረክብ ዘጽኑሕ ሎቱ ተብሎ ተነግሯል ፤ ምሳሌውን አሁን ያመጣል ። ዘፍ ፵፱ ፲ ።

፫ ወይሁዳኒ ወለደ ፋሬስሃ ወዛራሃ እምትዕማር
ዘፍ ፥ ፴፰፥፳፱ ፩ዜና ፪፥፬ ፥ ሩት ፬፥፲፰ ፥ ፩ዜና፪፥ ፫

፫ ይሁዳም ፋሬስን ዛራን ከትዕማር ወለደ ። የይስሐቅን ልደት በተናገረ ጊዜ ሳራን ፥ የያዕቆብን ልደት በተናገረ ጊዜ ርብቃን ፥ የይሁዳን የወንድሞቹን ልደት በተናገረ ጊዜ እለ ልያን እስ ራሔልን አላነሣም አሁን ደርሶ እምትዕማር እለ ምነው ቢሉ ይህች ምክንያት ያላት ናት ። ይሁዳ ሴዋ የምትባል ሚስት አግብቶ ኤርን አውናንን ሴሎምን ይወልዳል ፥ ኤር ማለት ፀሐይ ማለት ነው አውናን ማለት ወይን ማለት ነው ሴሎም ማለት መስተሳልም ማለት ነው። ለበኵሩ ለኤር ከአሕዝብ ወገን ትዕማር የምትባል ብላቴና እምጥቶ አጋባው አባቴ ማግባቴን ባይፈቅድልኝ ነው እንጂ ማግባቴንማ ቢፈቅድልኝ ከኃያላኑ ከእስራኤል ወገን ያጋባኝ አልነበረምን ብሎ ተጸይፎ የማይደርስባት ሆነ ። እግዚአብሔር ትዕቢት አይወድምና በዚህ ምክንያት ቀሠፈው ። ኋላ በአራት የሚሠራው በሕገ ልቡና ተገልጾለት ዓቅም ዘርዓ ለእኁከ ብሎ ለአውናን አጋባው ። እሱም ሥራውን እየሠራ ከዓፄ ዘርዕ በአፍአ ሆነ ልጅ ቢወለድ ለሱ ለስሙ መጠሪያ ይሆነዋል እንጂ ለኔ ምን ይሆነኛል ብሎ ፤ እግዚአብሔር ምቀኝነት አይወድምና ቀሠፈው ፥ በሳራ ወለተ ራጉኤል አስማንድዮስ የሚባል ጋኔን በጭንዋ አድሮ ሰባቱን ባሎቿን እንደገደለባት ይህች ብላቴና ልጆቼን ትጨርስብኛለች ብሎ በፈሊጥ ያሳናብታታል ። ሑሪ ቤተ አቡኪ ወንበሪ መበለቲኪ እስከ አመ ይልኅቅ ወልድየ ሰሎም ብሎ ፥ አድጎ ሳለ እንዳላደገ አድ

ርጎ ፣ እሷም እያዘነች ሂዳለች ። ማዘንዋ ማንዝሙት ቀረብኝ ብላ አይደለም ፣ እመቤታችን ጌታችን ከቤተ ይሁዳ ይወለዳሉ ሲሉ ትሰማ ነበርና ፡ ከባለተስፋ ቤት ወጥቼ ሄድሁ ብላ ነው እንጂ ፡ በዚያ ወራትና ሚስቱ ሴዋ ሞተችበት ። መዋዕለ ኀዘኑ ሲፈጸም ቴምናታ ወደምትባል ሀገር በጎቹን ሊያሸልት በሚሄድበት ጊዜ ናሁ ይሁዳ ሐሙኪ የዓርግ ውስተ ቴምናታ ከመ ይቅርፅ አባግኢሁ ብለው ነገሯት፤ ሴሎም እንዳደገ ያላትም ነገር እንዳልተፈጸመላት ባየች ጊዜ እንዳታስለኝ ላታስው ብላ ልብሰ ዘማ ለብሳ ጃንጥላ አስጥላ ድንኳን አስተክላም ቢሉ ክተመሳቀለ መንገድ ቆየችው ። እሥራኤል ሴት ሲያዩ አልፎ መሄድ አይሆንላቸውም ነበረና በጂ በዱኝ አላት ። በዚያውስ ላይ ሚስቱ ሦተተበት ማለት ለዚህ ይመቻል ። ምንት ትሁብኒ አስበ ደነስየ አለትው እሬኦ ለኪ ፩ መሐስዓጠሊ ፡ የፍየል ጠቦት እልክልሻለሁ አላት ። ሀበኒ አኀዘ መያዣ ስጠኝ አለችው ። ምን አለኝና ቢላት ፤ ቀለበትህን ኩፌትህን ዘንግህን ስጠኝ አለችው መያዣ ሰጥቶ ተገናኝቶ ይሄዳል ። እሷም ዘማ አይደለችምና ልብስዋን አሰልባ እንደ ጥንቷ ተቀመጠች ። የበግ መልከኛው ኢራስ አዶሎማዊ ይባላል ። ይኸን ጠቦት ወስደህ ለዚያች ዘማ ስጥተህ ገንዘባችንን ይዘህ ና ብሎላከው ። ቢፈልግ አጣት አይቴ ቤታ ለዘማ እያለ ይጠይቅ ጀመር ፡ እኛስ በሀገራችን ዘማም የለብን አሉት ። ተመልሶ አጣኋት አለው ፤ ብታገኛት ትሰጣት ነበር እንጂ ካጣሃትማ ገንዘባችን ኪኛ ፤ በዚያውም ላይ ዛሬስ የያዕቆብ ልጆች ጠገቡና አይቴ ቤታ ለዘማ እያሉ ዘማ ሲፈልጉ ይዞራሉ ሆነ ባሉን ነበር አለው ። ከሦስት ወር በኋላ ትዕማር መርዓትከ ፀንሰት በዝሙት ብለው ነገሩን ። በምን አውቀው ቢሉ ከሦስት ወር በኋላ ፅንስ እየገፋ ጡት እየጠቆረ ይሄዳልና ። በዚያ ወራት በአሕዛብ ሰልጥኖባቸው ነበረና በደንጊያ ወግራችሁ በእሳት አቃጥላችሁ ግደሏት ብሎ አዘዘ አድርሱኝ አለቻቸው የማያደርበዋት ሆነ ። እንኪያስ ኀልቅት ዘመኑ ዝ ኩፌት ዘመኑ ዝ ሕለት ዘመኑ ብላችሁ ስጡልኝ አለቻቸው ፤ ወስደው ሰጡት አይቶ ጸድቀተኒ ትዕማር ረታችኝ ፤ ጸድቀት እምኔየ ከኔ ይልቅ ተሻለች ከኔ የተነሣ ከበረች ብሎ ተናግሯል ። መንታ እንደፀነሰች አውቃ በምትወልድበት ጊዜ መወልዲቱን አስቀድሞ የተወለደውን በኩሩን እንድናውቀው ቀይ ሐር እሠሪበት አለቻት ፤ አስቀድሞ ዛራ እጁን ስደደ ፊትለ ለይ ሐር አሰረችበት ፣ ፋሬስ እሱን ወደኋላ ስቦ ተወለደ ። ፋሬስ ማለት ጣሽ ጠምሳሽ ክፍለት ፍልጠት ኃያል ማለት ነው ፤ ዕጹብ በእንቲአከ ማለት ነው ፤ ዕጹብ በእንቲአከም ማለት ያየነው ቀርቶ ያላየነው ወጣ ማለት ነው ። ዛራ ማለት ወለት ድክምት ማለት ነው ። ደክሞ ተወልዷልና ። ቅድመ ዘርኢናሁ ዝኒ ሠረቀ ማለትም ነው ። ቀይሕ ፊትለ ለይ ማለት ነው መልከ መልካም ማለት ነው ዛህራ ይላል በዓረብ መልከ መልካም ሲል ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው ፣ ይሁዳ የእግዚአብሔር አብ ኢራስ አዶሎማዊ የቅዱስ ገብርኤል በግዐ የእግዚአብሔር ወልድ ሕልቀት የሃይማኖት ኩፌት የአክሊል ምክሕለት የመስቀል ትዕማር የቤተ አይሁድ ። ትዕማር ማያዣ ይዛ ቀረች እንጂ ዋጋዋን አንዳላገኘች ቤተ አይሁድም ትንቢቱን ተስፋውን ሰምተው ቀሩ እንጂ በክርስቶስ አላመኑምና አንድም የምሳሌ ምሳሌ ። ትዕማር የምኩራብ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ትዕማር ልጆችን ክአባታቸው ከይሁዳ አገኘች እንጂ ። ከልጆች እንዳላገኘች ። ቤተ ክርስቲያንም ምዕመናንን ከእግዚአ ነቢያት ከእግዚአ ካህናት ከክርስቶስ አገኘች እንጂ ። ከነቢያት ከካህናት አላገኘችምና ። አንድም ትዕማር የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ትዕማር ከልጆችም ከባትም ዘርን እንዳልተጸየፈች ። ቤተ ክርስያንም ከሕዝብ ከአሕዛብ ከሐቃል ከሀገሬት ከግዙር ከቆላፍ ያመኑትን ሁሉ ትቀበላለችና ። ለዘመጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወጽኦ አፍኦ እንዲል ፣ ፋሬስ የአሪት ዛራ የወንጌል ምሳሌ ። ዛራ አስቀድሞ እጁን እንዳወጣ ። ወንጌልም በመልከ ጸዴቅ ታይታ ጠፍታለችና ። ፋሬስ እሱን ወደ ኋላ ስቦ እንደ ተወለደ በመካከል አሪት ተሠርታለች ። ዛራ በኋላ እንደተወለደ ወንጌል ኋላ ተሠርታለችና ። አደ ዛራ የቀሳውስት ፊትለ ለይ የሥጋው የደሙ ምሳሌ ። ይህንስ ለምን ይሻዋል ቢሉ ትዕማር በሃይማኖት እንደከበረች አሕዛብም በሃይማኖት እንዲከብሩ ለማጠየቅ በእስራኤል ዘለፋ ለአሕዛብ ተስፋ ሊመሆን ። በልደተ ሥጋ ይመካሉና፣ለኛስ ክርስቶስ ከትዕማር ተወልዶልን የለም ለማለት ። በዓቂበ ሕግ ይመካሉና የሕግ አፍራሽ ልጆች አይደላችሁምን ለማለት ። ክርስቶስ በዳዊት ከበረ ይላሉና ዳዊት በክርስቶስ ከበረ እንጅ እሱማ የትዕማር ልጅ አይደለም ለማለት ።

ወፋሬስኒ ወለደ ኤስሮምሃ ፡ ፋሬስም ኤስሮምን ወለደ ። ወኤስሮምኒ ወለደ አራምሃ ። ኤስሮምም አራምን ወለደ ።

፬ ወአራምኒ ወለደ አሚናዳብሃ ፡ ዘኍ ፡ ፯ ፡ ፲፪።
፬ አራምም አሚናዳብን ወለደ ፡ ወአሚናዳብን ወለደ ነዓሶንሃ ፡ አሚናዳብም ነዓሶንን ወለደ። ወነዓሶንኒ ወለደ ሰልሞንሃ ፡ ነዓሶንም ሰልሞንን ወለደ ።

፭ ወሰልሞንኒ ወለደ ቦኤዝሃ እምራኬብ ሩት ፬ ፳፪ ፡ ፩ ነገ ፡ ፲፮ ፩ ።

፭ ሰልሞንም ቦዔዝን ከራኬብ ወለደ ። በኦሪት ባያስ ይለዋል ። ከዚህ ቦዔዝ አለ እንደምነው ቢሉ ላንድ ሰው ሁለት ስም አለው ። አንድም በጸያፍ የገባ እሷንም በኦሪት ረዓብ ዘማ ይላታል፣ከዚህ ራኬብ አለ እንደምነው ቢሉ ላንዲት ሴት ሁለት ስም አላት ። አንድም በጸያፍ የገባ ፡ ራኬብ ማለት፣ ዘትትረከብ ለሁሉ ማለት ነው የይስሐቅን ልደት በተናገረ ጊዜ ሣራን የያዕቆብን ልደት በተናገረ ጊዜ ርብቃን የይሁዳን የወንድሞቹን ልደት በተናገረ ጊዜ ልያን ራሔልን አላነሣ ከዚህ ደርሶ ሰለምን አነሣ ቢሉ ምክንያት ያላት ናት ። ኢያሱ በሰጢን ሰፍሮ ሳለ ካሌብና ሰልሞንን ኢያሪኮን ሰልላችሁ ኑ ብሎ ሰደዳቸው ደጋ ደጋውን ሲሰልሉ አድረው ኢያሪኮ ከቆላው ሲደርሱ ነጋባቸው አሕዛብ አይተው ዐወቋቸው በምን ምክንያት ቢሉ ሲፈሩ አይተው፤ አንድም የጉበኛ ዓይኑ ባካና ነውና ዓይናቸው ሲባክን አይተው ። አንድም በልብሳቸው በአካላቸው እስራኤል ቅርጸ ቀላል ናቸው ልብሳቸውም ነጭ ነው ። አሕዛብ ግን ቁመተ ገፋፋ ልብሰ አዳፋ ናቸውና ። የኢያሪኮ ቅጽሯ ሰባት ነው ራኬብ ሕዝቡን ትቀበል ነበር ፡ ቢሉ ስድስቱን ወደውሥጥ አንዱን ወደውጭ አድርጋ ከስድስተኛው ዛኒጋባ ጥላ ትኖር ነበር መኳንንቱን ትቀበል ነበር ቢሉ ስድስቱን ወደውጭ አንዱን ወደውሥጥ አድርጋ ከስድስተኛው ዛኒጋባ ጥላ ትኖር ነበር ። ገብተው ሰውሪኝ አሏት ከሰገነት አውጥታ በቀርከሃ አቴና ጠቅላ አቆመቻቸው ። አንዲመጡ ዐውቃ ፍርፋሪ ጥላ ውኃ አፍሳ ትቆያለች መጥተው የእስራኤል ጉበኞች ካንቺ ገብተዋል ስጭን አሏት ። መግባትስ ገብተው ነበር ሕቀ በደሩከሙ አሀል ቀምሰው ውኃ ጠጥተው ሄዱ አለቻቸው ። መግባታቸውን ብታምንላቸው ፡ መውጣታቸውን ያመኑችልን መሰሏቸው ፤ ገብተን እንይ ሳይሉ ተመልሰው ሄዱ ። ኋላ ገብታ ትወርሱ ሀገሪን ወትቀትሉ ነገሥታቲን አለቻቸው በምን ዐውቀሽ አሏት ። እስመ እግዚአብሔር ወደየ ፍርሃተ ውስተ ልበ ኃያላኒን ። ኃያላኑ ሲፈሩ ሲሸበሩ ያድራሉ ። ላምላ ለስላ የሚከፈተው የብረት ላንቃ ከመዝ ሀለወነ ንትረኀው እያለ በገዛ እጁ የሚከፈት ሆነ ። ነገር ግን አሕዛብ ተድላ ሲያደርጉ እኔ አላደረግሁምና ደርባችሁ እንዳታጠፉኝ ማሉልኝ አለቻቸው ። አላቸውም ጠንቅቀው ይምላሉ ። እንች ለኛ እንዲህ ብለሽ ኋላ ለዘመዶችሽ ነግረሽ ፈጣሪያችን በቸርነቱ ቢያድነን ከመሐላ ንጹሐን ነን ከደጅሽ ሰንደቅ አላማ ትከዩበት ከመስኮትሽ ሐር ዝጊበት ሰውሽ ከቅጽር በአፍአ አይውጣ ወጥቶ ቢሞት በኛ ዕዳ የለብንም አሏት። እሷም መከራ ትስዳቸዋለች ፤ አሕዛብና ጉንዳን መንገድ ከያዘ አይለቅምና ሦስት ቀን በመንገድ አትሂዱ በዱር ሂዱ በመዓልትአትሂዱ በሌሊትሂዱ ብላ መከራ ሰደደቻቸው እንደነገረቻቸው አድርገው ኢያሱ ካለበት ደረሱ፣ እንደምን ሁናችሁ መጣችሁ አላቸው።እንዲህ ያለች ሴት አግኝተን ሰውራ ሰደደችን አሉት ። ከአሕዛብ ወገን እንዲህ ያለች ሴት መገኘቷ ፈቃደ እግዚአብሔር እንጂ ቢሆን ነው ብሎ አልዋለም አላደረም ዕለቱን ተነሥቷል መጀመሪያ አንድ ጊዜ ዙሮ ሰፈረ ከዚያም ጥቂት ጥቂት እልፍ እያለ ይሰፍራል ፡ እንዲህ እንዲህ እያለ እስከ ስድስት ቀን ይሰነብታል በሰባተኛው ቀን ኃያላኑን በቀኝ በግራ በፊት በኋላ አሰልፎ ካህናቱን ልብሰ ተክህኖ አልብሶ ታቦተ ጽዮንን አሸክሞ ስድስት ጊዜ ዙራችሁ በሰባተኛው የነጋሪት ድምፅ ስትሰሙ አውኩ ደንፉ አላቸው እንዲህ ማለቱ አሕዛብ ቍጡዓን ናቸው ወጥተው ይገጥመኛል ድል አደርጋቸዋለሁ ብሎ ነው ። ስድስት ጊዜ ዙረው በሰባተኛው የነጋሪት ድምፅ ሲሰሙ አወኩ ደነፉ ቅጽሩ ባራት ማዕዘን ፈረሰ ተናደ ፤ አሕዛብን አጥፍቶ ኢያሪኮን እጅ አድርጎ አድሯል ሰልሞን ከዚች ሴት ደጅ ጦሩን አቆመ ፤ ያች ያልኩህ ሴት ይሀች ናት ብሎ ግዳይ ጣለለት ባርኬልሃለሁ አግባት ። ልጅ ትወልድልሀ አለው ። እሱዋን አግብቶ ቦዔዝን ይወልዳል ፡ ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው ኢያሱ የጌታ ፤ ኢያሪኮ የምዕመናን ፤ አሕዛብ የአጋንንት ፤ ምሳሌ ። ኢያሱ አሕዛብን አጥፍቶ ኢያሪኮን እጅ እንዳደረገ ። ጌታም አጋንንትን ድል ነሥቶ ምዕመናንን ገንዘብ ለማድረጉ ምሳሌ ፡ መስኮት የከናፍረ ምእመናን ፡ ሐር

የሥጋው የደሙ ፤ ሰንደቅ ዓላማ የመስቀል ራኬብ የአሕዛብ ፤ ብዙ ወንድ ስታወጣ ስታገባ ኑራ ኋላ ባንድ በሰልሞን እንደ ተወሰነች አሕዛብም ብዙ ኃጢአት ሲሠሩ ብዙ ጣዖት ሲያመልኩ ኑረው ባንድ በጌታ እምነው ለመኖራቸው ምሳሌ ፤ ሰልሞንና ካሴብ የኦሪትና የወንጌል ምሳሌ ናቸው ሴላይነታቸው በዚህ ዓለም እንደሆነ ወንጌልና ኦሪትም የተሠሩ በዚህ ዓለም ነውና ፤ ይህንስ ለምን ይሻዋል ቢሉ ፤ ሐተታ እንዳለፈው እንደ ትዕማር በል ። ወቦዔዝኒ ወለደ ኢዮቤድሃ እምነ ሩት፡ ቦዔዝም ኢዮቤድን ከሩት ወለደ ። የይስሐቅን ልደት በተናገረ ጊዜ ሣራን የያዕቆብን ልደት በተናገረ ጊዜ ርብቃን የይሁዳን የወንድሞቹን ልደት በተናገረ ጊዜ እነልያን እነራሄልን አዳነማ ፤ ከዚህ ደርሶ ይህቶን አነጣ ምነው ቢሉ ። ምክንያት ያላቷ ናት ። አቤሜሌክ የሚባል ካህንም ጨዋም ነው ቢሉ ሚስቱ ኑኃሚን ትባላለች ኑኃሚን ማለት ፍሥሕት ጥዕምት ማለት ነው ልጆቻቸውም መሀሎን ኬልዎን ይባላሉ በረኃብ ምክንያት ደወለ ሞዓብ ተሰደው ሲኖሩ ለታላቁ ልጁ ለመሀሎን ሩትን ለታናሹ ለኬልዎን ዑርፋን አጋብቷቸው ሲኖር አስቀድሞ አባት ሞተ ከዚህ በኋላ ልጆቹ ሞቱ ። ኑኃሚን እንደዚህ ሁና ስትኖር ከእሥራኤል ወገን መንገደኛም ቢሉ ነጋዴም ቢሉ ሰው መጣ ሀገራችን እንደምን ሁነዋል ብላ ጠየቀችው ። ሀገራችንማ ለምቷል ቀንቷል ምን ታጥቆ የወይኑ ዘለላ ጋን ይመላ የስንዴው ዛላ እፍኝ ይመላ አላት ። ሠናይ ለብእሲ ለእመ ይከውን መቅብርቴ ውስተ ርስቱ እንዲል ፤ እንኪያስ ከሀገሬ እሞታለሁ እቀበራለሁ ብላ መንገድ ጀመረች ሁለቱ ምራቶቿ ተከተሏት ። አላትና ትተካልናለች አትሉኝ ፈጅቻለሁ ወልዳ ታደርስልናለች አትሉኝ አርጅቻለሁ ተመለሱ አለቻቸው ዑርፋ ከሞቱ እቴቴ ምን አለኝ ካማቴ የምትል ያልታደለች ናትና ስማት እጅ ነሥታት ተመለሰች ። ሩት ግን ከሞተ እቴቴ ምን አለኝ ካማቴ የማትል ደግ ሴት ናትና አገርሽ አገሬ ፈጣሪሽ ፈጣሪዬ ነው ከሞትሽበት እሞታለሁ ከተቀበርሽበት እቀበራለሁ ብላ ተከትላት ሄደች ። የሀገሯ ሰዎች ይወዷት ነበርና ኑኃሚን ኑኃሚን መጣች እያሉ ተቀበሏት ምን ፍሥሕት ጥዕምት ትሉኛላችሁ መራር ኀዘንት ትክዝት በሉኝ እንጂ ። መሊዐየ ወፃእኩ ወዕራቅየ ገባእኩ ፤ ከባል ከልጅ ወጥቼ ብቻዬን ተመለስኩ አለቻቸው። በሀገራቸው ሞቱን ካልሰሙ በታውን ለሌላ አይሰጡበትምና ቤቷን ጠርገውላት ገባች ። ሩት እየወጣች እየወረደች የሞያ እየዋለች ትመግባታለች ። ከዕለታት ባንድ ቀን ከቦዔዝ አዝመራ ሄዳ ስትለቅም ቦዔዝ ለሠራተኞች ምሳ አሲዞ መጣ እግዚአብሔር ምስሌከሙ አላቸው ኃይል ይሰጣችሁ ሲል ፤ እሆ በከመ ቃልከ ፤ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ አሉት ይህች ሴት ወዴት ናት ብሎ ጠየቀ በምን ምክንያት ቢሉ አሕዛብ መልከ መልካሞች ናቸውና በመልኳ ፤ አንድም አጥርቃ ስትለቅም አይቶ ፤ አንድም ስትፈራ አይቶ እስራኤል የሆነ እንድሆነ አራሪ ለማራሪ ማራሪ ለአዕዋፍ ይተዋሉ ። ከኑኃሚን ጋራ የመጣች ሞዓባዊት ናት አሉት ለዚችስ ገቢረ ሠናይ ይገባል ብሎ ጠርቶ ካጠገቡ አድርጎ ከእንጀራው ቆርሶ ከወጡ አጥቅሶ ሰጣት ወዲያው ሥራት ይሠሩላታል ከእንግዲህ ወዲህ አትከልክሏት ከመካከል ገብታ ትልቀም አትቅረጧት የሰበሰበችውን ተሸክማላት ጊዜ ሲያጋጥማችሁም ከምትጠጡት ስጧት ብሎ ይሠራላታል እርሷንም ይመክራታል ። እስራኤል ቀናተኞች ነን ካንዱ አዝመራ የዋለ ካንዱ አይውልም ። ትልዊዮን ለአዋልድዩ ። አዝመራው እስኪከተት ዛሬ ወዴት ውለዋል እያልሽ እየጠየቅሽ ከኔ አዝመራ ዋይ አላት እርስዋ ናሁ አመትከ ረከበት ሞገስ በቅድሜከ ብላ እጅ ነሣች ። የሰበሰበችውን ይዛ የተረፋትን በቀሚሷ ኪስ ቋጥራ ሄደች ብትሰፍረው ዐሥር መሰፈሪያ ሁኗል ያሥሩ ቃላት ምሳሌ ያን ሰጥታት ስተመገብ ዛሬ ከማን አዝመራ ውለሽ ነሯል አለቻት ። ከቦዔዝ አዝመራ አለቻት ። አንች ባታውቂው ነው እንጂ ፤ እሱማ የባልሽ የመሀሎን ርስት ጕልት ያለ በእሱ እጅ እንጂ ነው እንቺ ለኔ በጕሥራ ብትሠሪ እኔም ላንቺ በጕሥራ መሥራት ይገባናልና ዐውድማ የሚጥ ልበትን ቀን ጠይቀሽ ንገሪኝአለቻት። ጠይቃ ነገረቻት ገላዋን አጥባ ሽቱ ዘግባ ደኅና ልብስ አልብሳ የሴቶች ወግ አድርሳ መክራ ትሰዳታለች ። እሥራኤል ሲበሉ ቢያይዋቸው አይወዱምና ከክምር ሥር ተሠውረሽ እምሽተሽ ሲተኛ ቀርበሽ ከእግሩ ሥር ተኚ ። አንች ማነሽ ይልሻል እኔ ባሪያህ ሩት ነኝ አወራረስ አቆራረስ ይገባኛል ብየ መጥቻለሁ በዬው ከዚህ በኋላ እምላክ እስራኤል ያለው ይደረግልሻል አለቻት ። እንደ ነገረቻት እስኪበሉ ከክምር ስር ተሰውራ ቆይታ ሲተኛ ቀርባ ከእግሩ ስር ተኛች አንቺ ማነሽ አላት እኔ ባሪያህ ሩት ነኝ አወራረስ አቆራረስ

ይገባኛል ብዬ መጥቻለሁ አለችው ከቀደመው ደግነትሽ የዛሬው ይብሰጥ አረጋዊ ነው ብሰሽ ወደ ሕፃን መልከ ከፉ ነው ብለሽ ወደ መልከ መልካም ድኃ ነው ብለሽ ወደ ባለጠጋ አለመሄድሽ ነገር ግን ከኔ ይልቅ አወራረስ አቆራረስ የሚገባው አለ ያ ቢያደርገው አደረገው ያ ባያደረገው ሕያው እግዚአብሔርን እንዳደርግልሽ ። አሁንም ሰው ሳያይሽ ሂጂ ብሎ እንዳታፍር ፮ መሥፈሪያ ስጥቶ ሰዷታል ። የሄቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌ ፡ ሲነጋ ቦዔዝ ሰው ሰብስቦ ባደባባይ ተቀምጦ ያን ሰው ሲያልፍ አይቶ አስጠራው ። የመሀሉን ርስት ጉልት ያለ ባንተ እጅ ነው ይህችን ብላቴና አግብተህ ስሙን የሚያስጠራ ልጅ አትወልድምን አለው ። ቀዳሚ ተሐምሦ ዘዚአየ ወዳግም ተሐምዎ ዘዚአከ እውነትህ ነው አስቀድሞ አወራረስ አቆራረስ የኔ ነው ። ቀጥሎ ያንተ ነው ። ዘዚአየ ተሐምዎ ተሐምው አንተ የኔን አንተ ውሰደው ከሁለት ዣፍ ያለች ወፍ ሁለት ክንፏን ትነደፍ እንዲሉ እኔስ የሁለት ቤት ማተናት የሁለት ልጅ ማሳደግ አይሆንልኝም አለው ፡ እንኪያስ በእሬት የሚገባውን አድርገህ ስጠኝ አለው ፡ ጫማውን አውጥቶ ይሰጠዋል ። ጫማ ለእግር ቤዛ እንደሆነ ኃይል ቤዛ የሚሆን ልጅ ቀረብኝ ሲል በዚህም ቤተ ፍቱሐን እማዕን ተብለው እስከ ፯ ቤት ድረስ ይሰደቡበታል ጺቅ ይሉበታል ጽቁንህ ፈሎ ፤ ሕዝቡም መርቀው ያጋቡታል። የያዕቆብን ቤት በልያ በራኄል ምክንያት ሰልጅ በክብት እንዳነጸው ያንተንም ቤት በዚች ብላቴና ምክንያት በልጅ በከብት ይነጽልህ ብለው መርቀው ይሰጡታል ። እርስዋን አግብቶ ኢዮቤድን ይወልዳል ። ኢዮቤድ ያለችው ኑኃሚን ናት ኢዮቤድ ማለት መጽንዒ ርስት ጸዋሬ ርስዓን መርሥዔ ኃዘን ማለት ነው ። ይህንስ ለምን ይሻዋል ቢሉ ሐተታ እንዳለፈው እንደ ትዕማር ባል ። ከዚህም ጌታን ከነዚህ መወለድ አያሳድፈውም እሳቸውን ያጸራቸዋል ያከብራቸዋል እንጂ ፡ ብርሃን ፀሐይ ከሸለል በወደቀ ጊዜ ሸለሉን ያጸራዋል ይሰነግለዋል እንጂ ብርሃን ፀሐይን እንዳያሳድፈው ።

ወኢዮቤድኒ ወልደ ዕሴርሃ፤ ኢዮቤድም ዕሤይን ወለደ ። ወዕሤይኒ ወለደ ዳዊትሃ ንጉሠ ዕሤይም ንጉሥ ዳዊትን ወለደ ፡ ሐተታ ፤ በሚያመጣው ሰሎሞንሃ ንጉሠ ሮብዓምሃ ንጉሠ ፡ አብያሃ ንጉሠ አይል አሁን ደርሶ ዳዊትሃ ንጉሠ አለ ምነው ቢሉ ፤ ዳዊት ሥርወ መንግሥት ነውና ፤ ሥርወ መንግሥትማ ሳኦል አይደለም ቢሉ ትንቢት የተነገረ ለዳዊት ነውና ትንቢትማ ለሳኦልስ ብንያም ተኩላ መሣጢ ይበልዕ ሲሳዮ በነግህ ተብሎ ተነግሮለት የለም ቢሉ ያንማ እንጂ ወፍና ሠርክ ይሁብ ሲመላእክቲሁ ባለው አፍርሶታል ።

፮ ወዳዊትኒ ንጉሥ ወለደ ሰሎሞንሃ እምነ ብእሲተ ኦርዮ ፤ ፪ ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፳፬ ።

፮ ዳዊት ንጉሥም ከኦርዮ ሚስት ከቤርሳቤህ ሰሎሞንን ወለደ ። ኤሊያስ ሴቶቹ ከአረማውያን ወገን ቢሆኑ ነው ፡ እነዚህማ እሱ ዕብራዊ እሱዋ ዕብራዊት ስለምን እንዲህ አለ ቢሉ ። ዳዊትማ ጉልማሳ አስገድሎ የጉልማሳ ሚስት ቀምቶ ማማውን ግርማውን ቢፈሩ ኃጢአቱን ሳይገልጽበት ቀረ እንዳይሉት ሐዋርያ መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ እንደሆነ ለማጠየቅ ፡ አንድም በተነሳሕያን ፍርሃት እንሌለባቸው ለማጠየቅ ፡ አዳምን ያሀል ሰው በድሎ ንስሐ ቢገባ ተማረ ። ዳዊትን ያሀል ሰው በድሎ ንስሐ ቢገባ ተማረ ። ጴጥሮስን ያሀል ሰው ክዶ ንስሐ ቢገባ ተማረ እናንተም ንስሐ ብትገቡ ትድናላችሁ ለማለት ፡ አንድም በዓቂበ ሕግ ይመካሉና እናንተስ የሕግ አፍራሽ ልጆች አይደላችሁምን ለማለት ። ክርስቶስ በዳዊት ከበረ ይላሉና ፤ ዳዊት በክርስቶስ ከበረ እንጂ እሱማ ጉልማሳ አስገድሎ የጉልማሳ ሚስት ቀምቶ አልነበረም ለማለት ፡

፯ ወሰሎሞንኒ ወለደ ሮብዓምሃ ፫ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፵፫ ፡ ። ፲፬ ፡ ፴፩ ፡ ፲፭ ፡ ፰ ።

፯ ሰሎሞንም ሮብአምን ወለደ ወሮብዓምኒ ወለደ አብያሃ ሮብዓምም አብያን ወለደ ። ወአብያኒ ወለደ አሳፍሃ ። አብያም አሳፍን ወለደ ።

፰ ወአሳፍኒ ወለደ ኢዮሳፍጥሃ ።

፰ አሳፍም ኢዮሳፍጥን ወለደ ። ወኢዮሳፍጥኒ ወለደ ኢዮራምሃ ኢዮሳፍጥም ኢዮራምን ወለደ ወኢዮራምኒ ወለደ አካዝያስሃ ኢዮራምም አካዝያስን ወለደ ወአካዝያስኒ ወለደ ኢዮአስሃ ፡ አካዝያስም ኢዮአስን ወለደ ፤ ወኢዮአስኒ ወለደ አሜስያስሃ ኢዮአስም አሜስያስን ወለደ ሐተታ ፤ አካዝያስን ፡ ኢዮአስን አሜስያን የሚጽፍም የማይጽፍም ይገኛል ። የጸፈ እንደሆነ የተመቸ ። የተወ እንደሆነ በሀገራቸው አንድ አ እንጂ ሁለት አ አይገኝምና አና አ አሳስቶት በሀገራቸውስ ስንኳን ሁለት አ አራት አ ይገኛል ብሎ ዝያና ዝያ አሳስቶስ ፤ አንድም መምለኪያን ጣዖት ናቸውና ስማቸው በመጽሐፍ መጻፍ አይገባውም ብሎ ። ይህማ እንዳይሆን ጌታ ግብር ይጸየፋልን ብሎ ፤ ለቀጥር ይመቸኝ ብሎ ፤ ለቀጥርስ ይመቸኝ ቢል በኒህ ዕጣ ወጥቶባቸዋልን ቢሉ ። ግድፈተ ጸሐፊ ነው ።

ወአሜስያስኒ ወለደ አዝያንሃ ዘተሰምየ አዛርያስ ፤ አሜስያስም አዛርያስ የተባለ አዝያንን ወለደ ፤

ሕዝቡ በፍና ተማልቆ፤ በማይገባ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ማዕጠንተ ወርቅ ይዞ ከቤተ እግዚአብሔር ገብቶ ቢያጥኑ አዛርያስ ይባሉ ብለውታልና ፤ በፍና ተማልቆ ስለተናገሩ አዛርያስ የተባለ አለ ፤ እንድም አዛርያስ በሉኝ ያለ ኦዝያንን ወለደ ። የአዛርያስን ሥራ ልሥራ ማለት አዛርያስ በሉኝ ማለት ነውና ፤ በዘመኑ ሊቀ ካህናቱ አዛርያስ ይባላል በቀኙ ይቆመጣል ምነው ይለዋል ፡ ወካህን ይነብር በየማኑ እንጂ ይላል ይለዋል ። ፍርዱን ይገሥበታል ምነው ይለዋል እምነ መንግሥት የዓቢ ክህነት እንጂ ይላል ይለዋል። ክሱ የሚበልጥ ልብስ ይለብሳል ፤ ምነው ይለዋል ፤ ካህናቲከ ይለብሱ ጽድቀ እንጂ ይላል ይለዋል ። ባባቴ ከቤተ መንግሥት ብወለድ በናቴ ከቤተ ክህነት እወለድ የለምን ብሎ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ማዕጠንተ ወርቅ ይዞ ሊያጥን ሲገባ ሕዝቡ ተው አይገባም አይሆንም አሉት ። ንጉሥ ነውና ተጋፍቶ ገባ ፤ ሊያጥን ጢስ ቅታሬው ቢነካው ከግንባሩ ለምፅ ወጣበት በሻሽ ቢሸፍነው ከሻሹ ላይ ወጣ ። እሥራኤል ለምፅ የያዘውን ስንኳን ሊያነግሡት ሊገናኙት አይወዱምና ወአውፅእዎ ለአዝያን ውስተ ቤተ ሐፍሶት እንዲል ። ቆሳ አወጡት ወኢዮአታም ወልዱ የዓቅብ ቤተ መንግሥት ወይኴንን ሕዝበ ምድር እንዲል ልጁን ኢዮአታምን አነግሡዋል ይህንንስ ለምን ይሻዋል ቢሉ ፤ ሐተታ እሱ ካስተማሩት ትምህርት ከሠሩለት ሥራት ቢወጣ እንዲህ ያለ መከራ አገኘው ፤ እናንተም ካስተማርናችሁ ትምህርት ከሠራንላችሁ ሥራት ብትወጡ እንዲህ ያለ መከራ ያገኛችኋል ለማለት ፤

፱ ወአዝያንኒ ወለደ ኢዮአታምሃ ፪ ኀጹ ፳፮ ፡ ፳፫ ፡ ፳፯ ፡ ፱ ፡ ፳፰ ፡ ፳፯

፱ ኦዝያንም ኢዮአታምን ወለደ ። ወኢዮአታምኒ ወለደ አካዝሃ ። ። ኢዮአታምም አካዝን ወለደ ። ወአካዝኒ ወለደ ሕዝቅያስሃ አካዝም ሕዝቅያስን ወለደ ።

፲ ወሕዝቅያስኒ ወለደ ምናሴሃ ። ፪ ኀጹ ፴፪ ፡ ፴፫ ፡ ፴፫ ፳ ፡ ፳፭ ።

፲ ሕዝቅያስም ምናሴን ወለደ ። ወምናሴኒ ወለደ አሞፅሃ ። ምናሴም አሞፅን ወለደ ። ወአሞፅኒ ወለደ ኢዮስያስሃ አሞፅን ኢዮስያስን ወለደ ።

፲፩ ወኢዮስያስኒ ወለደ ኢኮንያንሃ ወአኃዊሁ አመ ፍልሰተ ባቢሎን ፡ ኀጹ ፴፮ ፡ ፩ ፡ ፱ ።

፲፩ የባቢሎን ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም በዘመቱ ጊዜ የኢየሩሳሌም ሰዎች ተማርከው ወደ ባቢሎን በወረዱ ጊዜ ኢዮስያስም ኢኮንያንን ወንድሞቹን ወለደ ሐተታ ወንጌላዊ ስቶን ዘንግቶ የልጅ ልጁን ልጁ ብሎ አጎቶቹን ወንድሞቹ ብሎ እንደነገው ጊዜ የተደረገውን ስልደቱ ሰጥቶ ተናገረ ቢሉ ፤ ስቶም ዘንግቶም አይደለ ልማድ ይዞ ነው እንጂ የልጅ ልጁን ልጁ አለ ልማድ ይዞ ፤ ያዕቆብ ከላባ ኮብልሎ ሚስቶቹን ልጆቹን ይዞ በመጣ ጊዜ ላባ ሦስት ቀን የሄደውን አንድ ቀን ገሥግሦ ደርሶ ፤ ለምንት ትሰርቀኒ ደቂቅየ ወአዋልድየ ከመ ዘበኵናት ፄወወሚመ ኢይደልወኒኑ አበዓም ደቂቅየ ወአዋልድየ ብሎታል ። አጎቶቹንም ወንድሞቹ አለ ልማድ ይዞ የአብርሃም ቤተሰቦችና የሎጥ ቤተሰቦች በሣር በውኃ ምክንያት ቢጣሉ ፡ ለምንት ንትጋመፅ እንዘ አኃው ንሕነ በበይናቲነ ለእመ አነ የማን ሐር አንተ ፀጋመ ፡ ወለእመ ፀጋም አነ ሐር አንተ የማነ ብሎታል እንደ ነገው የተደረገውን ስልደቱ ሰጥቶ ተናገረ ። ይህንም ልማድ ይዞ ነው ፡ ደቂቅከ ይነብሩ ፈላስያነ ብሔረ ነኪር ወይቀንይዎሙ ግብጽ ፬ ፻ ዓመተ እንዳለ ። በግብጽ የሚኖሩት ሁለት መቶ ዐሥራ አምስት ዘመን ሲሆን በከነዓንየሚኖሩትን ደርቦ ስደቱን ከሰሙት ብሎ እንደተናገረ ። አሁንም ፄዋዌውን ከሰሙት ብሎ እንደ ነገው ጊዜ የተደረገውን ስልደቱ ሰጥቶ ተናገረ ። ታሪክ ኢዮስያስ በነገሠ ባሥራ ሦስት ዓመት ኤልያቄም ኢኮንያንን ይወልዳል ። በዚህ ጊዜ ነቢዩ ኤርምያስ ይህ ልጅ በነገሠ ጊዜ ፄዋዌ ይደረጋል ብሎ ትንቢት ተናግሯል ፤ የኢዮስያስ መላ ዘመነ መንግሥቱ ሠላሳ አንድ ነው ። ኢኮንያን በተወደ ባሥራ ስምንት ኢዮስያስ በነገሠ በሠላሳ አንድ ዓመት ፈርዖን ኒካው ዘመተ ኒካው ማለት አንካሳማለት ነው ። ስለ ምን ዘመተ ቢሉ ንጉሠ በብንግን ለመውጋት ። እንድም መንግሥት ለማጻረስ ፤ ከመ ያብጽሕ አዴሁ ላዕለ ፈለገ አፍራጢን እንዲል ፤ ቀድሞ የሀገራችን ነገሥታት መንግሥት ለማጻረስ እዞሰም ይወጡ እንደነበረ ፡ መጥቶ ሰፈረ ። ንጉሠ እስራኤል ካንተ ፀብ የለኝምና መንገድ ስጠኝ አለው ። ለሕዝቡ ቢነግራቸው እኛስ ሀገራችንን የአሕዛብ መገሥገሻ አናደርጋትም አሉት ። አይሆንም በሌላ መንገድ ሂድ አለው እንግዲያውማ የመጣሁበትን ሳላደርግ የምመለስ ነኝ ብሎ ኃለኛ ንጉሥ ነውና ተጋፍቶ ሄደ ፤ ኢዮሲያስም ስልፍ ቆየው ኢዮሲያስ በንፍጥ ተመቶ ወደቀ አሽከሮናቸውን ይዘው ወደ አምባ ተጠጉ እሱም ፀብ የለውምና አልፎ ሄደ አምባ ገብተው ኢዮሲያስን ቀብረው ልጁን ዮአክስን አንግሠው ተቀመጡ ንጉሠ በብንግን ወግቶ ሦስት ወር ኑሮ ግብሩን ተገብሮ ወደ ኢየሩሳሌም ቢመለስ አገሪቱን ጫብላ አገኛት የዚህች ሀገር ኃያላን እንደ ቀትር ንብ ይናደፉ ነበረ ወዴት ሄደዋል ብሎ ጠየቀ ፤ እንድም የቀሩት መጥን ሲያገቡልኝ እነዚህ የማያገቡልኝ በምን ምክንያት ነው ብሎ ጠየቀ ። እንድም የዚች አገር ንጉሥ ቀመቶ ነበር እሱን ሞተ ብሎ ጠየቀ ። እሱማሙቶ አምባ ገብተው እሱን ቀብረው ልጁን ዮአክስን አንግሠው ተቀምጠዋል ብለው ነገሩት ። በሀገራቸው ሥራት ፈሊጥ የሰም የገደለ ያንግሥ የዘመተ ይመለስ አይሉም ብሎ አምባውን

ሰብሮ ዮአክስን አሥሮ ኤልያቄምን አንግሦላቸው ሄድዋል ኤልያቄም ማለት ቆመ ለነ እግዚአብሔር ማለት ነው ፣ ኢቆመ ለከሙ ሲል ኢዮአቄም ብለሎታል ፤ ግብጽ ከሄደ በኋላ ሦስት ዓመት ይገብርለታል ወተቀንየ ኢዮአቄም ንጉሠ ይሁዳ ለንጉሠ ግብጽ ሠለስተ ዓመተ እንዲል ። በአራተኛው ዓመት ናቡከደነጾር ዳር ዳር መውጋት ጀመረ መንገድ ተያዘብኝ ብሎ ግብር ነሣ ባምስተኛው ዓመት መጥቶ ግብር አለው ። ንጉሥ ፍርድ ልበስ ፈርኦን ኒካው አባቴን ገድሎ ወንድሜን አስሮ እኔን አንግሦ ግብሩን ተገብሮ ሄደ አንድ ባሪያ ለሁለት ጌታ መገዛት እንደምን ይሆንለታል አለው ፤ አሕዛብ ፍርድ ጠነቀቅን ባዮች ናቸውና የዚያን ያንካሳ መዳረሻ ሳላሳይህ የዕለት ራት የጧት ቀለበት ልትለኝ አይገባህም ብሎ ግብጽ ወርዶ ፈርኦን ኒካዑን ገድሎ ሦስት ዓመት ኑሮ ባቢሎን ዘግብጽ አሰኝቷት ተመልሰዋል ። ከተመለሰም በኋላ ሦስት ዓመት ይገብርብርለታልአሥር አንድ ዓመት ይሆናል ከዚህ በኋላ ሞት ቢያምረው በሰማይ የለ ዱር በእሥራኤል የለ ግብር ብሎ ግብር ነሣው ፣ እሱም ተከል ለማየት ወጥቶ ሳለ ከለዳውያን ገድለውታል ። አንድም በእደ እግዚአብሔር ታሞ ሙቷል ፤ ልጁን ኢኮንያን አነግሡ ኢኮንያን ሦስት ወር እንደ ነገሠ ናቡከደነጾር ተመልሶ መጣ ይተወኛል መስሎት ወባት ገባ ፤

እሱን አስሮ ሕዝቡን ማርኮ ሲሄድ እንቱ ናታን ከመንገድ ቆይቶ ልጅ ሳለሁ የልጅ ልጅ አዋቂ ሳለሁ አላዋቂ ፤ ታላቅ ሳለሁ ታናሽ አንግሠውብኝ ነበር የዚህን ግፍ አይቶ እግዚአብሔር መንግሥትን ላንተ አሳልፎ ከሰጠህ ንጉሥ ፍርድ ልበስ አለው ምን ላድርግልህ አለው ፤ አንግሠኝ አለው፤ ሕዝቡን ማርኬ እወስዳቸዋለሁ በማን ልንግሥሃለሁ አለው በሀገሬ እኔ አውቃለሁ ተክል በሚኰተኰቱት በገበራርት አንግሠኝ አለው፤ አንግሦት ሄዷል በሙን ሴዴቅስያስ አለው ። ባተከደኝ ፣ ማለት ነው ። እሱም እምባውን እያጸና ግብሩን እየሰደደ ስምንት ዓመት ኖረ ፤ በዘጠነኛው ዓመት እንደወንድሙ ሞት ቢያምረው በእሥራኤል የለ ግብር በሰማይ የለ ዱር ብሎ ግብር ነሣው ። አስቀድሞ ፀባኢተ ሞዓብን ፀባኢተ ሶርያን ሰዶ አስከበበው ፤ ኋላም እሱ ፲ት ዓመት ከ፰ ወር ይከበዋል ፤ ወተገፍትዓት ሀገር ይላል የዘመን ረኃብ ሰው ቀዩ ይጠቁራል ጥቁሩ ይነጣልና ። አንድም እኩሉ እንገብር እኩሉ እንዋጋ በማለት ተለያዩ ። ናቡከደነጾር ሥራት ሠርቶላቸው ነበር ሰው የሞተባቸው እንደሆነ ፤ መቃብር አይከልከሉ እያወጡ በየርስታቸው ይቅበሩ ብሎ በዚያ ልማድ ዋይ ሸሽ ተበላሽ ብላችሁ ይዛችሁኝ ውጡ አላቸው ። ዋይ ሸሽ ተበላሽ እንያሉ ይዘውት ሲሄዱ ያ ምንድነው ብሎ ጠየቀ። በምን አውቆ ቢሉ ሰው በዝቶ ነበርና ። አንድም ፍርድ ያደላባት ቤት ነግራበት የእሥራኤል ንጉሥ ሞቶ በሠራህላቸው ሥራት ሊቀብሩት ይወስዱታል አሉት ። የወዳጅን እንጂ አስከሬን አጥቦ ገንዞ መቅበር ይገባል ወደኔ አምጡት ብሎ አስመጥቶ መግነዙን ፈተው ቢያዩት ዓይኑቆለል ቆለል ሲል ተገኝቷል ወተናገሮ ፍትሐ እንዲል ወቀሰው ። መርጬ ባነግሥህ ምነው ከዳኸኝ ። ከከዳኸኝስ በኋላ ወይ እችላለሁ ብለህ አትዋጋ ወይ አልችልም ብለህ አትገብር በዚያውስ ላይ እኔን ከዚህ እኑረህ ወዴት ልትሄድ ኑሯል ብሎ መኳንንቱን ፍረዱልኝ አላቸው ። እችላለሁ ብሎ አይዋጋ አልችልም ብሎ አይገብር ሞት ይገባዋል አሉ ፍርድስ አላወቃችሁም ሞቱ ስብእሲ ዕረፍቱ ሞትማ ዕረፍት አይደለምን እኔ አውቃለሁ ብሎ ፯ ለመንግሥት የደረሱ ልጆች ነበሩት ከፊቱ በሠይፍ አስመታቸው፤ እሱንም ከፉ ባየበት ዓይኑ በጎ አይይበት ብሎ ሁለት ዓይኖቹን በፍላት አውጥቶ ትብትብ አሸክሞ ዱር ለዱር በፈረስ ጭራ እያስጎተተ ባቢሎን ይዞት ወርዷል ከዚያም ባቄላ ሲፈጭ ከወፍጮ ስር ልቡ ፈርሶ ሞቷል ወይከውን መቃብረክ ታሕተ እግረ ማኅረፅ ያለው የነቢዩ ቃል ይደርስ ይፈጸም ዘንድ የዮአክስ ሦስት ወር የኢኮንያን ሦስት ወር ከመንፈቅ የሴዴቅያስ ዓሥርዓመትከመንፈቅአሥሬአንድዓመት የኤልያቄም ዓሥራ አንድ ። የኢዮስያስ ዓሥራ ስምንት ፤ አርባ ይሆናል ፤ ይኸ ሁሉ ዘመን እያለ ዬዋዌውን ክሰሙት ብሎ እንደ ነገሠ ጊዜ የተደረገውን ለልደቱ ሰጥቶ ተናገረ አንድም ከዚህ ሁሉ ሐተታ ለመዳን ዘአመ ፍልሰተ ባቢሎን የሚል ይገኛል እሥራኤል ተማርከው ባቢሎን በወረዱ ጊዜ የነገሠ ኢኮንያንን ወለደ ይህ አያሳስትም ። ዬዋዌ ሥጋው ለዬዋዌ ነፍሱ ምልክት እንደሆነ ሚጠተ ሥጋው ለሚጠተ ነፍስ ምልክት ነውና። እሥራኤል ተማርርከው ባቢሎን መውረዳቸው ነፍሳት ገሃነም ለመውረዳቸው ምሳሌ ነውና እሥራኤል ከባቢሎን መውጣታቸው ነፍሳት ከሲኦል ከገሃነም ለመውጣቸው ምሳሌ ነውና ። ኤልያቄምን ዮሚጽፈውም የሚተወውም አለ ፥ የተወው እንደ ሆነ መጽሐፈ ኤርምያስን አቃጥሎ ነበርና በመጽሐፍ መጻፍ አይገባውም ብሎ ። ይኸማ እንዳይሆን ጌታ ግብር ይጸየፋል እንጂ ባሕርይ ይጸየፋልን ብሎ ለቀጥር ይመቸኛል ብሎ ያውስ ፤ ቢሆን

በሱ ዕጣ ወጥቶበታልን ብሎ ። ግድፈተ ጸሐፊ ነው ይህን ለምን ይሻዋል ቢሉ አሳቸው ከሠራላቸው ሥራት ካስተማሯቸው ትምህርት ቢወጡ እንዲህ ያለ መከራ አገኛቸው ። እናንተም ከሠራንላችሁ ሥራት ካስተማርናችሁ ትምህርት ብትወጡ እንዲህ ያለ መከራ ያገኛችኋል ለማለት ።

፲፪ ወእምድኅረ ፍልሰተ ባቢሎን ኢኮንያንኒ ወለደ ሰላትያልሃ ።

፲፪ የኢየሩሳሌም ሰዎች ተማርከው ባቢሎን ከወረዱ በኋላም ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ ፤ ሐተታ ምንዋ ኢየዓርግ ብእሲ እምውስተ ዘርዐ ዘይነብር ዲበ መንበሩ ይል የለምን ቢሉ፥ አይነግሥም አለ እንጂ አይወለድም አለ ፤ ያውስ ቢሆን አይነግሥም ያለው ሴዴቅያስ ኢኮንያንን ነው እንጂ ፤ ኤልያቄም ኢኮንያንን ነውን ፤

ወሰላትያልኒ ወለደ ዘሩባቤልሃ ሰላትያልም ዘሩባቤልን ወለደ

፲፫ ወዘሩባቤልኒ ወለደ አብዩድሃ

፲፫ ዘሩባቤልም አብዩድን ወለደ ።
ወአብዩድኒ ወለደ ኤልያቄምሃ አብዩድም ኤልያቄምን ወለደ ። ወኤልያቄምኒ ወለደ አዛርሃ። ኤልያቄምም አዛርን ወለደ ።

፲፬ ወአዛርኒ ወለደ ሳዶቅሃ ።

፲፬ አዛርም ሳዶቅን ወለደ ።
ወሳዶቅኒ ወለደ አኪንሃ ፤ ሳዶቅም አኪንን ወለደ ። ወአኪንኒ ወለደ ኤልዩድሃ ፥አኪንም ኤልዩድን ወለደ ፥

፲፭ ወኤልዩድኒ ወለደ አልዓዛርሃ

፲፭ ኤልዩድም አልዓዛርን ወለደ ወአልዓዛርኒ ወለደ ማትያንሃ አልዓዛርም ማትያንን ወለደ ወማትያንኒ ወለደ ያዕቆብሃ ማትያንም ያዕቆብን ወለደ።

፲፮ ወያዕቆብኒ ወለደ ዮሴፍሃ ፈኃሪሃ ለማርያም እንተ እምኔሃ ተወልደ እግዚእ ኢየሱስ ዘተብህለ ክርስቶስ ።

፲፮ ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለ ኢየሱስ ከእሷ የተወለደ የእመቤታችን እጮኛ የሚሆን ፥ ዓቃቤሃ ተለአኪሃ እንጋልጋይዋ ጠባቂዋ የሚሆን ዮሴፍን ወለደ መገናኛው ጉንዱ አልዓዛር ነው አልአዛር ማትያንንና ቅስራን ይወልዳል ማትያን ያዕቆብን ያዕቆብ ዮሴፍን ይወልዳል ቅስራ ኢያቄምን ኢያቄም እመቤታችንን ፤ በሀገራቸው ሴትና ወንድ አቀላቅሎ መቍጠር የለምና ሥርዓት አፈረሰ ይሉኛል ብሎ በዮሴፍ እንጻር ቆጠረ እሷንም እንዳትቀር በቅጽል አመጣት፥ ሐተታ በ፫ ቤት እንድትታጭ ማድረጉ ስለ ምን ቢሉ በልማድ ፥ አዋልደ ሰለጳድ ከሙሴ ዘንድ ሄደው አባታችን የሞተ በበደሉ ነው እኛ ከነገር አልገባንምና ርስት አካፍለን ስሙን እናጽራው አሉት ፥ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ። ርቱዓ ይቤላ አዋልደ ሰለጳድ፡ ሀቦን መክፈልቶን ማዕከለ አኃዊሆን አለው ፤ እሥራኤል ይኸነን ሰምተው ሴት የያዘችው ነገር ከሁሉ ይደርሳል ከእንግዲህ ወዲህ ርስት ከርስት ትውልድ ከትውልድ እንደተፋለሰ ዐወቅ አሉት ፥ ሁለተኛ አመለከተ ። አስተዋስቦን ዘእምቅሩቦን ባባታቸው ወገን በሦስት በሦስት ቤት እየተጋቡ እንዲወርሱ አድርግ ብሎታልና በነዚያ ልማድ ፤ አንድም ፄዋዌ ቢጸናባቸው ወንዱ ለሴቲቱ ሴቲቱ ለወንዱ የማያዝኑ ሁነዋል በተዘምዶተ ሥጋ ላይ የግቢ ተዘምዶ የተጨመረ እንደሆነ ጥኂት አይሄድም ያዝንላታል ብለው የሚያጋቧቸው ሁነዋልና በዚያ ልማድ በዚያስ ላይ እንድትታጭ ማድረጉ ስለ ምን ቢሉ ፥ ኃይል አርያማዊት ባሏት ነበርና ፥ ወንድ ከወንድ ተገኘ ባሉ ነበርና ከመ በብሂሎቱ ፍሑርተ ብእሲ ያግሕድ ከመ እግዝእትነ ማርያም በአማን ብእሲት ይእቲ እንዲል ፤ አንድም ፅንሱን ከአጋንንት ለማሳሳት ዐውቀው ቢሆን ብዙ ፅንስ ባበላሹ ነበርና ፤ እንድም መስተመይናን ዝሁላን አእምሮ አይሁድ ሰብሳብ ርኩስ፥ ይላሉና ። ንጹሕ እንደሆነ ለማጠየቅ ። አንድም በመከራዋ ጊዜ ሊከተላት ከርስት ገብቶ ሊቆጠርላት ከውግረት ሊያድናት ፤ ዮሴፍ ምክንያት ባይኖራት በድንጊያ ወግረው በገደሏት ነበርና ፤ ከፅዕለትም ሊያድናት ፤ ወይእንዛሁ ሰብዑ እንስት ለ፩ዱ ብእሲ ወይብላሁ እክለዚአነ ንሴሰይ ወልብሰ ዚአነ ንትዓረዝ ዳዕሙ ይሰመይ ስምከ በላዕሌነ ወእኅድግነ ዘንተ ጽዕለተ እንዲል ፤ ይህንም ፪ ሊቃውንት አሙሩ ፈቃደ ዮሴፍ ወሠለስቱ ሊቃውንት አሙሩ ፈቃደ ሥላሴ ይላል ። ሁለቱ ሊቃውንት የተባሉ ዮሴፍ ለጊዜው እገባለሁ መስሎት ነበር ብለው የጻፉ ሳዊሮስ ዘአስሙናይን ያዕቆብ ዘሮሃ ናቸው ። ፫ቱ ሊቃውንት የተባሉ ሥላሴ ንጽሕናውን ባወቁ አስጠብቀውታል ብለው የጻፉ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ዮሐንስ አፈወርቅ ናቸው ዘተብህለ ክርስቶስ አለ ይህም ስም ብቻ የትስብእት ብቻ የመለኮት አይደለም ። ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ቢሆን የወጣለት ስም ነው እንጂ ወእነግር እነሂ ከመ ኢመፍትው አስምዮ ለቃለ እግዚአብሔር ክርስቶስ ዘእንበለ ትስብእት ፤ ወኢለትስብእት ዘእንበለ መለኮት ክርስቶስሃ ይሰመይ ወእምቅድመ ትሥጉት እልቦ ዘይሰምዮ በዝንቱ ስም ለቃለ እግዚአብሔር ክርስቶስ እንዲል ፥ በዝንቱ ስም ተሰምዩ ነቢያት ቅቡዓን እስመ ስመ ክርስቶስ ይትበሃል ሳዕለ ብዙኃን ጸታ ከመ ነገሥተ እሥራኤል ወካህናቲሆሙ

ከመ አሮን ወዳዊት ወዘኃረየሂ ከመ ሥርዓተ ቈርበ ውእቱ ይላልሳ ቢሉ ፣ ይኸንም እንጂ ፣ ወተቀብዖሰ በመንፈስ ከመ ካህናተ ሐዲስ ውእቱ ወላዕለ ዘተወልደ እምእግዝእትነ ማርያም ይትብህል እንበይነ ተዋሕዶ ዘኮነ ሊመለኮት በእንተ ዘተሠገወ እምድንግል ህየንተ ቅብዓተ ቅብዕ ባለው አፍርሶታል ። እንዲህ ከሆነ ማን ሲያይ ተናግሮታል ቢሉ አንዱን ሲያይ ፤ ገብርኤል ስሙ ዘአምኃ ለማርያም ዘበትርጓሜሁ አምላክ ውእቱ እንዲል ፤ ኤልን ሲያይ ፤ ይህም አምላክ ሰው ቢሆን የወጣለት ስም ነው ። ወዝ ስም ዘውእቱ ክርስቶስ ወፍካሬሁ ቅብዓት ምስለ አምጣነ ትስብእቱ ረከቦ ለዋሕድ እንዲል ፤ ከበረ መባሉም በሥጋ ነው ። ወቅብዓቱሰ ዘተወክፈ በትስብእቱ ይእቲ ወኢኮነ ቅብዓቱ አምሳለ ቅቡዓን እለ ይትቀብዑ ይፈቅዱ ቀሪበ ኀቤሁ ለከዊነ ወልድና ውእቱሰ አምላክ ውእቱ በጠባይዒሁ ዘእንበለ ፈቂድ እንዲል ቦ እለ ይቤሉ አምቅድመ ተዋሕዶ ወቦ እለ ይቤሉ እምድኅረ ተዋሕዶ እንዲል ፤ ወገባሪሁሰ ለውእቱ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ እስመ ውእቱ ቀብዖ ወተዋሕደ ቦቱ አምላክ ቃል ያለውን ይዘው ተቀብቶ ተዋሀደ የሚሉ አሉ ፤ ተሠጊዎ ነሥአ ቅብዓተ በዘተሰብአ ተቀብዓ ያለውን ይዘው ሰው ሁና ተቀብቶ ተዋሕደ የሚሉ አሉ ። ነገር ግን እንዲህ አይደለም ሲቀባም ሲዋሐድም አንድ ጊዜ ነው ። ከመ ቅጽበተ ዓይን ፤ አለሰ የአምኑ ርቱዓ ይሜህሩ ከመ ተቀበዓ ቃል በሥጋሁ ወእምአመ ኮነ ቃል ሥጋ አሚሃ አስተርአየ በመንፈስ ቅዱስ እንዲል ።

፲፯ ወኵሎንኬ ትውልድ እምአብርሃም እስከ ዳዊት ፲ወ፬ቱ ፡

፲፯ ከአብርሃም እስከ ዳዊት ዐሥራ አራት ትውልድ ነው ፤ ወእምዳዊት እስከ ፍልሰተ ባቢሎን ትውልድ ፲ወ፬ቱ ። ከዳዊት እስከ ፄዋዌ ፲፬ ትውልድ ነው ። ወእምፍልሰተ ባቢሎን እስከ ክርስቶስ ትውልድ ፲ወ፬ቱ ።

ከፄዋዌ እስከ ክርስቶስ ዐሥራ አራት ትውልድ ነው ፤ ወኵሎንኬ ትውልድ እምአብርሃም እስከ ክርስቶስ ፵ወ፪ቱ ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ መላው አንድ ሁኖ ቢቈጠር አርባ ሁለት ነው ። ፲ወ፬ቱ ፲ ወ፬ቱ ፲ወ፬ቱ ይላል ። አርባ ሁለት ይሆናል ። ዐሥራ አራት ዐሥራ ሰባት አሥራ ሁለት ይላል አርባ ሦስት ይሆናል ። ዐሥራ አራት ዐሥራ ሰባት ዐሥራ አራት ይላል አርባ አምስት ይሆናል ፣ አርባ ሁለት ያለ እንደ ሆነ ሁለቱን አግብቶ ሦስቱን ነገሥታት አውጥቶ ፣ አርባ ሦስት ያለ እንደ ሆነ ከሦስቱ አንዱን አግብቶ ሁለቱን አውጥቶ ። አርባ አራት ያለ እንደሆነ ከሁለቱ ከእመቤታችንና ከኤልያቄም አንዱን አግብቶ አንዱን አውጥቶ ፣ አርባ አምስት ያለ እንደሆነ ፣ መላውን አግብቶ ፣ ከፍ ብሎ አርባ ስድስት ዝቅ ብሎ አርባ አንድ ቢል ግድፈተ ጸሐፊ ነው ተርትሮ የቈጠረውን ደምሮ ፣ ደምሮ የቈጠረውን ተርትሮ ቈጠረ ደምሮ የቈጠረውን ተርትሮ ተርትሮ የቈጠረውን ፣ ደምሮ ባይቈጥር አይሁድ ወንጌላዊ ተርትሮ መቈጠር እንጂ መደመር መደመር እንጂ ተርትሮ መቁጠር አይሆንለትም ብለው ደገኛዪቱን ሕገ ወንጌልን ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና ፣ አንድም ተርትሮ መቍጠር የሦስትነት ደምሮ መቍጠር ያንድነት ምሳሌ ። አንድም ተርትሮ መቍጠር እንደ ሦስት ምስክር ደምሮ መቍጠር ቃሉ አንድ የመሆኑ ምሳሌ ፣ ልማ በሥሉስ ጥፉ በሥሉስ አንዱሉ ፣ አንድም በዳንኤል ልማድ ፸ ሰንበታተ አድኅኖሙ ለሕዝብከ ያለውን ተርትሮ የቆጠረውን ደምሮ ደምሮ የቆጠረውን ተርትሮ እንደ ቈጠረ ፣ አንድም በሦስቱ ክፍለ ዘመን የተቈጠረው ባንድ በጌታ እንደተፈጸመ ለማጠየቅ በዘመነ አበው በዘርዕከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ተብሎ ፣ በዘመነ ነገሥት እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ በዘመነ ካህናት መቅደስ ትትሐነጽ እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ወእምዝ ትትመዘበር ተብሎ የተነገረው ተስፋ ባንድ በጌታ እንደ ተፈጸመ ለማጠየቅ ፣ አንድም ተርትሮ ቆጠረ ሥጋዊ ምግብና ሲለዋወጥ መጥቷል ፣ በዘመነ አበው ምክር ተግሣፅ ሁኑዋል ያባት ለልጅ ያልፍ ነበር መጻሕፍት አልተጻፉም ፣ በዘመነ መሳፍንት ፣ መጻሕፍት ተጽፈዋል መስቀል መቁረጥ ሁነዋል ። በዘመነ ካህናት እንደ ሁለቱም ሁኑዋል እንደ ዘመነ አበው ምክር ተግሣፅ ሁኑዋል ። ያባት ለልጅ የማያልፍ ሁኑዋል ። እንደ ዘመነ መሳፍንትም መስቀል መቀረጥ ሁኑዋል መጻሕፍት ተጽፈዋል ። ደምሮ ቆጠረ መንፈሳዊ ምግብና ምንም በካህናት በኤጲስ ቆጶሳት እጅ ቢሆን አልተለወጠም አንድ ነው ለማለት ፤ አርባ ሁለት ባለው ለሰሎሞን ስድስት እርከን ያላት አትሮንስ ነበረችው እሱ በስድስተኛዪቱ ሁኖ ነገር ሲሰማ ሲፈርድ ይውል ነበር ስድስቱ እርከን በሱባዔ ሲገቡት አርባ ሁለት ይሆናል ። ያርባ ሁለቱ አበው ምግብና ሲፈጸም ጌታ ሰው የመሆኑ ምሳሌ ፣ ሰሎሞን የጌታ አትሮንስ የእመቤታችን ምሳሌ፣ አርባ ሦስት ባለው ለደብተራ አሪት አርባ ሦስት አእማድ ነበሯት አርባ ሦስት አዕማደ ቅስብእት አበው ሲፈጸሙ ጌታ ሰው ለመሆኑ ምሳሌ ። አርባ አራት ባለው እሥራኤል ባአርባ አራተኛው ጉዞ ሰጢን ሰፍረው ርስታቸውን አይተው አድረዋል ፣ እንደዚህ ምዕመናንም ካአርባአራተኛዪቱትውልድ ከእመቤታችን

ተወልዶ ርስታቸው ጌታን አይተዋልና አርባ እምስት ሺው ባርባ እምስተኛ ጉዞ አየርስታቸው ገብተዋል ፤ እንደዚሁ ሁሉ ምእመናንም አርባ እምስተኛ ትውልድ የሚሆን ርስታቸው ጌታን ይወርሳሉና ።

በእንተ ልደተ ክርስቶስ ።

፲፰ ወለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመዝ ውእቱ ልደቱ ፣ የነትዕማርን የነራኬብን የነሩትን ሲናገር

፲፰ መጥቶ ነበርና ፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደቱ እንዲህ ነው አለ፣ ከጥንት ሲነገር ሲያያዝ የመጣው ነው እንጂ ፣ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ አይደለም ። ወሶበ ተፍኅረት ማንሻ ፣ እንድም ወለእግዚእነስ ይላል ፣ በዘር በሩካቤ የሚወለዱ የአበውን ልደት ሲናገር መጥቶ ነበርና ፣ የጌታትን የኢየሱስ ክርስቶስ ግን ልደቱ እንዲህ ነው አለ ፤ እንበለ ዘር ነው ፣ ከመዝ ያለውን ያመጣዋል ፣ ወሶበ ተፍኅረት እሙ ማርያም ለዮሴፍ ፣ ሉቃ ፩፣፳፯ እናቱ እመቤታችን ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ።

ዘእንበለ ይትቃረቡ ተረክበት ጽንስተ እንዘባ ውስተ ማኅፀና እመንፈስ ቅዱስ ።

ዘእንበለ ይትቃረቡ ዘእንበለ ይትራከቡ ይላል ፣ እሱ ሴት እንደሆነች ሳያውቃት እሷ ወንድ እንደሆነ ሳታውቀው ዮሴፍ ጠባቂ ሳላት አጋዥ ሳትሻ እንድም ድንጋሌ ሥጋ ድንጋሌ ነፍስ ሳላት ፣ እንድም ቢእምዘ ካላት ከባሕርይዋ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች ወገባሪሁሰ ለውእቱ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ እስመ ውእቱ ቀብዖ ወተዋሐደ ቦቱ እምሳክ ቃል እንዲል ይህ እም በሲሆን ነው ፣ እስመ እም ይትረኮም ለኀበ ብዙኅ ፍና እንዲል ስማያት ወም ምድር ተፈጥሩ እምእግዚአብሔር አዳም ወሔዋን ተፈጥሩ እምእግዚአብሔር እንዲል እመንፈስ ቅዱስም ቢል በመንፈስ ቅዱስ ተከፍሎ ኑሮበት አይደለም ፣ አንጻት ሲል ነው እንጂ ፣ ወእኮ ዘበቱ ሥጋ ለመንፈስ ቅዱስ ፣ አላ መንፈስ ቅዱስ አንጽሐ ሥጋሃ ለማርያም ወረሰያ ድሎተ ለተወክፎ ቃለ አብ እንዲል ። አነፃትም ቢል ኑሮባት አነፃት ማለት አይደለም ከለከላት ሲል ነው እንጂ ። ውእቱሰ ንጹሕ እምኑ ፫ቱ ግብራት እለ ሥሩዓን በእጓለ እመሕያው ወእሙራን በሙ ዘውእቶሙ ሩካቤ ወዘርዕ ወስስሎተ ድንግልና እንዲል ከለከላትም ቢል ብታደርገው ዕዳ የሚሆንባት ሁኖ አይደለም አሳደረገችውም ሲል ነው እንጂ ። ከዚያ ሁሉ ወኮነ ይስሐቅ ያፈቅሮ ለዔሳው እስመ ዘውእቱ ነዐወ ይሴሰይ ብሎ ወያዐቅብስ ንጹሕ እምዝንቱ ይላል ። አሁን በኤሳው አድኖ መብላት ዕዳ ሁኖበትን ነው ፤ ያዕቆብን አላደረገውም ድልድል ቅምጥል ከቤት ዋይ ነው ሲል ነው እንጂ ። ልደቱን በዘር ያላደረገው እንበለ ዘር ያደረገው ስለምን ቢሉ ቀዳማዊ ልደቱን ለመግለጥ ። እምስት ሺህ እምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከእመ ቤታችን ያላባት መወለዱ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለእናት እንደተወለደ ያስረዳልና ፤ ልደት ቀዳማዊ ተዓውቀ በደኃራዊ ልደት እንዲል ። ዳግመኛ በዘር በሩካቤስ ተወልዶ ቢሆን ዕሩቅ ብእሲ ባሉት ነበርና ፣ ሶበሰ ተወልደ በሩካቤ ብእሲ ወብእሲት ዘከማየ ብዙኃን እምተኃዘብዎ ወእምረሰይዎ ሐሰተ እንዲል ። ያውስ ቢሆን ልደቱን ተፈትሖ ካላት ያላደረገው ተፈትሖ ከሌላት ያደረገው ስለምን ቢሉ ፤ ትንቢቱ ምሳሌው እንደተፈጸመ ለማጠየቅ ትንቢት ፣ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም አዳም ከኅቱም ምድር ተገኝቷል ጌታም በኅቱም ማኅፀን ለመገኘቱ ምሳሌ ነውና ። ሔዋን ከኅቱም ገቦ ተገኝታለች ጌታም ከኅቱም ማኅፀን ለመገኘቱ ምሳሌ ናትና ። ቤዛ ይስሐቅ በግዕ ከኅቱም ጉንድ ተገኝቷል ። ቤዛ ዓለም ክርስቶስም በኅቱም ማኅፀን ለመገኘቱ ምሳሌ ነውና ፤ ጽምዓ እሥራኤልን ያበረደ ውኃ ከኅቱም ኩኩሕ ተገኝቷል ጽምዓ ነፍሳትን ያበረደ ማየ ሕይወት ጌታም በኅቱም ማኅፀን ለመገኘቱ ምሳሌ ነውና ። ጽምዓ ሶምሶንን ያበረደ ውኃ ከኅቱም መንሰከ አድግ ተገኝቷል ፣ ጽምዓ ነፍሳትን ያበረደ ማየ ሕይወት ጌታም በኅቱም ማኅፀን ለመገኘቱ ምሳሌ ነውና ፤ ትንቢቱን ዐውቆ አናግሯል ። ምሳሌውንም እንጂ ዐውቆ አስመስሏል ፣ ፍጻሜው እንደምን ነው ቢሉ ከመ ትኩን መራሒተ ለሃይማኖት ዓባይ እንጂ ይላታል ። ድንግል ወእም ስትባል መኖሯ ፤ እምሳክ ወሰብእ ሲባል ለመኖሩ ምሳሌ ነውና ስትወልደው ማኅተመ ድንግልናዋ አለመለወጡ ፤ ሰው ሲሆን ባሕርየ መለኮቱ ሳለመለወጡ ምሳሌ ናትና።

፲፱ ወዮሴፍሰ ፈኀሪሃ እስመ ጻድቅ ውእቱ ኢፈቀደ ይክሥታ

፲፱ እጮኛዋ የሚሆን ኅቃቢሃ ተስእኪሃ ፣ አገልጋይዋ ጠባቂዋ የሚሆን ዮሴፍ ግን ደግ ነውና ሲገልጣት ሊገልጥባት አልወደደም ።

አላ መከረ ጽሚተ ይኅድጋ ። ትቷት ሊሄድ ወደደ እንጂ ፤ ሐተታ ፤ ይህን ደግነቱን ያስቀርበታልን በአራት ታዞ የለምን ሚስቱን የጠረጠራት እንደሆነ ውኃ በመንቀል የገብስ ዶቄት አድርጐ ሚስቱን ይዞ ይሄዳል ከመድረኩ ስትደርስ ሊቀ ካህናቱ ከንብሽን ግለጭ ይላታል ይግለጥብኝ በይ ሲላት ነው። በአራቱ የሚደገም አለ ያንን ደግሞ ሕራረ ዕጣኑን ጨምሮ በጥብጦ ባልሽ የጠረጠረሽን አድርገሽው እንደሆነ ሥጋሽ ይበጥ ቁርበትሽ ይላጥ አጥንትሽ ይርገፍ ፣ አላደረግሽው እንደሆነ በወንድ ልጅ ተበከሪ ብሎ ይሰጣታል ። እስዋም መርገሙ ይደረግብኝ በረከቱ ይሁንልኝ ብላ ትጠጣዋለች ፣ ይህ ደግ

ነቱን ያስቀርበታልን በአራቱ ታዞ የለም ቢሉ ዮሴፍ ጻድቀ ወንጌል ነው እንጂ መቸ ጻድቀ ኦሪት ነዋ ።

፳ ወእንዘ ዘንተ ይሔሊ ናሁ አስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ለዮሴፍ በሕልም ።

ታሪክ፡እመቤታችን የብፅዓት ልጅ ናት ሦስት ዓመት ሲሆናት አባት እናቷ ወስደው ለካህናት ሰጡ።ካህናትም ተቀብለው አክብረው ከቤተ መቅደስ ያኖሯታል ዐሥራ ሁለት ዓመት ትኖራለች ከዚያ፫ ከዚያ ፲፭ ዐሥራ አምስት ዓመት ይሆናል ። አይሁድ ሰም ቀኝነት አያርፉምና ይሀች ብላቴና መጠነ አንስት አደረሰች ቤተ መቅደሳችንን ታሳድፍብናለች ትውጣልን አሉት ፣ ዘካርያስ ሂዶ እንደምን ትሆኝ አባት ወደ እግዚአብሔር አመልክትልኝ አለችው ቢያመለክት ከነገደ ይሁዳ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን በትር ሰብስበህ ከቤተ መቅደስ አግብተህ አውጣው ምልክት አሳይልሃለሁ አለው ። ቢሰበስብ ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ለሁለት ሽህ ዐሥራ አምስት የጎደለው ማለት ነው ያን አግብቶ ቢያወጣው ከዮሴፍ በትር ፣ አ ዮሴፍ ዕቀባ ለማርያም የሚል ተገኘ። ዕጣም ቢያወጡ ለሱ ወጣ ፤ ርግብም መጥታ በራሱ ላይ ዐረፈች ፣ እንደ ሦስት ምስክር ያም ሆነ ያም ሆነ ከእግዚአብሔር አግኝተን የሰጠንህን ከእግዚአብሔር አግኝተን እስክናሰናብትህ ወስደህ ጠብቅ አትንካ ብለው ሰጡት ። ይዟት ሄደ ጊዜው ዓፀባ ነበርና ንግድ ሂዶ ሦስት ወር ኑሮ ቢመለስ ዮሐንስ የሚባል ፈላስፋ ወዳጅ ነበረው ሊጠይቀው መጣ ተጨዋውተው ሲሄድ ሊሸኘው ወጣ ፤ ይህች ብላቴና ፀንሳለች ካንተ ነው ከሌላ አለው ። እኔስ እንኳን ነቢብ ገቢር ሐልዮም አላውቅባት አለው ። እንኪያስ ፀንሳለች ገብተህ ጠይቃት አለው ። በምን ዐውቆ ቢሉ ፈላስፋ ነውና በመልኳ ገብቶ አወሰተ እሥራኤል መኑ ቀረጸ አክናፈ ድንግልናኪ ወአመኀበ መኑ ፀነስኪ ብሎ ጠየቃት ። እመንፈስ ቅዱስ አለችው ፤ ነገሩ ቢረቅበት ከደጁ ወድቆ የሚኖር ደረቅ ግንድ ነበርና ተክላ አለምልማ አሳይታዋለች ። በዚያውስ ላይ አዕዋፍን ከባሕርያቸው እንዲራቡ አዕዋምን እንዲያፈሩ የሚያደርግ ማን ይመስልሃል አለችው ነገሩን ተረዳው ። ከዚህ በኋላ ለበዓል የሚወጡበት ጊዜ ደረሰ ። ትቻተ ብወጣ ያደረገችውን ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ እንዲሉ ያደረገውን ዐውቆ ትቷት መጣ ይሉኛል ይዣት ብወጣ ሴሰነች ብለው በደንጊያ ወግረው ይገሉብኛል እያለ ፤ ወወድቀ ዮሴፍ ውስተ ጽኑዕ መዋግደ ሕሊና ይላል ይህነን ሲያወጣ ሲያወርድ ። ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ነገረው (ሐተታ) ህልም ከሦስት ወገን ነው ከሐሞት ከመልአክ ከሰይጣን የሚገኝ ነው ፤ ከሐሞት የሚገኝ በልቀም ደም ሳፍራ ሳውዳ የሚባሉ ሐሞታት አሉ ። በልቀም እሳታዊ ፤ ደምማያዊ ፣ ሳፍራ ነፋሳዊ ፣ ሳውዳ መሬታዊ ነው ፣ እኒህ በሠለጠኑ ጊዜ በየግብራቸው ሲያሳዩ ያድራሉ ፣ ከሰይጣን የሚገኝ እንደ ሄሮድስ በስደቷ ጊዜ ከዚህ ዋለች ከዚህ አደረች እያለ ይነግረው ነበር ፣ ከመልአክ የሚገኝ እንደ ዮሴፍ እንደ ፈርዖን እንደ ናቡከደነፆር ፣

እንዘ ይብል አ ዮሴፍ ወልደዳዊት ኢትፍራህ ነሢአታ ለማርያም ፍኀርትከ ፣

እ ቃለ አክብሮ ቃለ አንሥሮ ቃለ አራኅርሖ ይሆናል። ቃለ አንሥሮ ፤ ኦሐናንያ አኢብዳን ሰብአ ገላትያ ፤ ቃለ አክብሮ አ ጳውሎስ ምንተ ትቤ እ አኃውየ ፍቁራን ፣ ቃለ አራኅርሖ አድንግል እዘከሪ አዮሴፍ ያለው ይህ ነው ። የርኅሩኅ የዳዊት ልጅ ዮሴፍሆይ አንተህ ናትና ራራላት ፣ እንድም የጥቡዕ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ከካህናት እጅ እንደ ተቀበልህ ከእደ መንፈስ ቅዱስ መቀበልን አትፍራ ነሢአታ ባለው አብነት አዕርጎታ ለውፅአታ ዓቂቦታ ተልእኮታ ይላል ። እስመ እም ፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበመንበርከ ያለው ትንቢት እንደተፈጸመ ለማጠየቅ ዳዊትን አነሣው ።
እስመ ዘይትወለድ እምኔሃ እመንፈስ ቅዱስ ውእቱ፣ ከሱዋ የሚወለደው በግብረ መንፈስ ቅዱስ ነውና ማቴዎስ እመንፈስ ቅዱስ ያለውን ሉቃስ መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመፅእ ላዕሌኪ ያለውን ፣ ኢሳይያስ መንፈስ እግዚአብሔር ዘላዕሌየ ዘበእንቲአሁ ቀብዓኒ ያለውን ሊቁ ዛቲሙ ትርጓሜሃ ለቅብዓት ፣ እስመ መንፈስ ቅዱስ አንጽሐ ሥጋሁ ለአዳም ብሎ ወስዶታል ፣ ንጽሕን ክብር የሚል ወዴት አለ ቢሉ ። ወሠዓርኮ እምንጽሑ ይላል ።

፳፩ ወትወልድ ወልደ ፣

፳፩ ወንድ ልጅ ትወልዳለች ፣ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ግብረ ሐዋ ፬፡ ፲፪ ።

ወትሰምዮ ስሞ ኢየሱስሃ ። ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለች ። እስመ ውእቱ ያድኅኖሙ ለሕዝቡ እምኃጣውኢሆሙ ፣

ወገኖቹ እሥራኤልን በኃጢአት ከመጣባቸው ፍዳ ያድናቸዋልና ፣ ኢየሱስ ብሎ ንባቡን ፣ ያድኅኖሙ ብሎ ስሙን ከነትርጓሜው ተናገረ ። ኃይሎ ለስም ወፍካሬሁ አብጽሐ ቅዱስ መልአክ እንዲል ።

፳፪ ወዝንቱ ኵሉ ዘኮነ ከመ ይትፈጸም እምኀበ እግዚአብሔር ፣

፳፫ በነቢይ እንዘ ይብል ፣ ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ፣ ኢሳ ፯ ፣ ፲፬ ።
አጸፋውን ለወንጌላዊ የሰጡ እንደሆነ ፳፪ ፣ እመቤታችን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ትፀንሳለች በግብረ መንፈስ ቅዱስ ትወልዳለች ብሎ መልአኩ ለዮሴፍ መንገሩ ፣ ፳፫ ነቢይ ድንግል ትፀን

፳፫ ወትወልድ ወልደ ብሎ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው ፤ አጸፋውን ለመልአኩ የሰጡ እንደሆነ እመቤታችን በድንግልና መጽነስዋ በድንግልና መውለድዋ እግዚአብሔር በነቢዩ አድሮ ነቢይ ከእግዚአብሔር አግኝቶ ተገልጾለት ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ብሎ የተናገረው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው ፤ ወይሰመይ ስሙ ዐማኑኤል ። ስሙም ዐማኑኤል ይባላል ። ዘበትር ርጓሜሁ እግዚአብሔር ምስሌነ ።

ዐማኑኤልም ማለት እግዚአብሔር ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነሥቶ ከኛ ጋራ አንድ ሆነ ማለት ነው ፤ ሐተታ ወንጌላዊ የሚጽፍላቸው በቋንቋቸው በዕብራይስጥ ነው ። መልአኩም ለዮሴፍ የሚነግረው በዕብራይስጥ ነው ። ምን ይተረጉማል ቢሉ ያበ ቅዱስ ቄርሎስ የንስጥሮስን ነገር ሲያስፈርድ አንተ ኀድረት ካልህ ዐማኑኤል ያለውን ንባብ እግዚአብሔር ምስሌነ ብሎ የተረጐመ ወንጌላዊ አበላ ፤ ሕስወኬ ይመስይ ወንጌላዊ ዘይተረጉም በኀቤሆሙ ብሎ ረትቶበታል ይተረጉምላቸዋል ትርጓሜው ግን በቋንቋቸው ካህናቱ የሚያውቁት ሕዝቡ የማያውቁት እንደ ጥሬ ያለ አለና ያንን ማጽናት ማጕላት ነው መጽሐፍ በወ በዘ ያጕላል በወ ቢያጕላ ፍሥሐ ወኃሤት ፍቅር ወሰላም ፤ በዘ ሲያጕላ ምንት ብከ ዘኢንግእከ እምካልዕከ ወምንት ብከ ዘኢኮነ ውሁበ ለከ ይላል እንድም ዮሐንስ ወንጌላዊ የማቴዎስ ወንጌልን ለሰብአ ኢሳንሳን ተርጕሞላቸዋል ፤ በዚያ ጊዜ ዐማኑኤል ንባቡ ከእብራይስጥ እግዚአብሔር ምስሌነ ትርጓሜው ከኤላንሳን መጥቶልናል፤ ዐማኑኤልን የመሰለ የኤላንሳን ንባብ ሳይመጣልን ቀርቷል ። እንድም የሀገራችን መላሽ ዐማኑኤል ያለውን የዕብራይስጡን ቋንቋ ወደግእዝ ቢመልሱት እግዚአብሔር ምስሌነ ማለት ነው ፤ እግዚአብሔር ምስሌነ ማለትም ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነሥቶ ከኛ ጋራ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ማለት ነው ብሎ ተርጕሞታል ፤ ወተንሢአ

፳፬ ዮሴፍ እምንዋሙ ገብረ በከመ አዘዞ መልአከ እግዚአብሔር ።

፳፬ ዮሴፍ ከዕንቅልፉ ተነሥቶ መልአኩ ያዘዘውን እንዳዘዘው አደረገ ።

ወነሥአ ለማርያም ፍኅርቱ ፤ ይዛት ውጣ እንዳለው ይዟት ወጣ ፤ ጠብቅ እንዳለው ጠበቀ ተቀበል እንዳለው ተቀበለ

፳፭ ወኢየእምራ እስከ አመ ወለደት ወልደ ዘበኩራ ።

፳፭ መጻሕፍት በዙር ያሉላት ልጅዋን እስከ ትወልድ ድረስ አላወቃትም ፤ አእመራ አዳም ለሔዋን አእመራ ሕልቃና ለሐና ብእሲቱ እንዲል የግብር ዕውቀት አላወቃትም ፤ ከወለደች በኋላስ ዐወቃት ማለት ነውን ቢሉ ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው ኢተመይጠ ቋዕ እስከ አመ ነትገ ማየ አይኅ ኢወለደት ሜልኮል እስከ አመ ሞተት እንዲል ሜልኮል ከሞተች በኋላ ወለደች ማለትን ነው ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው ፤ አንድም ባንድ ኀብረ መልክእ አላወቃትም ሲል ነው ሥጋዌው በብዙ ኀብረት ትንቢት የተነገረለት በብዙ ኀብረ አምሳል የተመሰለለትን እሱን እንደፀነሰች ለማጠየቅ መልኳን ይለዋውጠው ነበርና ። ቦ ኢሜ ታሕመስምል ወቦ ኢመ ትጸዓዱ እንዲህ ስንኳን የፀሐየ ጽድቅ ሰሌዳ ድንግልን ሙሴንስ እንኳ ኃሳፊ ብርሃን ቢሳልበት እስራኤል ተገልበብ ለነ ብለውታል አንድም ኢያእመረ ይላል ወልድ የተባለ እሱ ድንግል የተባለች ልርስዋ እንደ ሆነች አላወቀም አጸፋውን ለወንጌላዊ የሰጡ እንደሆነ ምነው መልአኩ ነግሮት የለምን ቢሉ ፤ ፩ ከሆነ ብሎ ፩ ዓይን እያስረግጥ ፤

፩ ምስክር ኢያስደንግጥ እንዲሉ ፤ አጸፋውን ለመልአኩ የሰጡ እንደሆነ ነቢዩ ነግሮት የለምን ቢሉ ድንግል አለ እንጂ እሷን አለው ወልድ አለው እንጂ አምላክን አለው ብሎ አምስት ነገር አይቶ ኢበኪረዳ ድረስ ኢያእመረ አላወቀም ። ምጽአተ ሰብእ ሰገል ዘምስለ እምኃ ፤ ሑረተ ኮከብ በካልእ ፍና ፤ ሥርቀተ ስብሐተ እግዚአ ዓቢይ ቅዳሴ መላእክት ፤ ፍርሃተ ኖሎት ይህን አይቶ እስኪረዳ ድረስ ዐላወቀም ። በኩራ በጥንት በበዓት በተቀድሶ ። ወጸውዐ ስሞ ኢየሱስሃ ።

እስከ አመ ወለደት ወእስከ አመ ጸውዐ መጻሕፍት በዙር ያሉላት ልጅዋን እስከትወልድ ስሙንም ኢየሱስ ብለው እስኪጸሩት ድረስ ኢያእመረ፤አንድም ዘበኩራ ወዘጸውዐ መጻሕፍት በዙር ያሉላት ስሙንም ኢየሱስ ያሉት ልጅዋን እስከትወልድ ድረስ ኢያእመረ ። ወእኮ በከመ ቃየን ዘእምእኩይ ወቀተሎ ለእኅሁ እንዲል ። ወዘቀተሎ ሲል ፤
በእንተ ምጽአተ ሰብአ ሰገል ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወተወሊዶ እግዚእ ኢየሱስ በቤተ ልሔም ዘይሁዳ በመዋዕለ ሄሮድስ ንጉሥ ናሁ ሰብእ ሰገል መጽኡ እምብሔረ ጽባሒ ። ሉቃ ፪ ፣፯ ።

፩ ሄሮድስ ነግሦበት በነበረ ዘመን የይሁዳ ዕፃ በምትሆን በቤተ ልሔም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ሳለ በተወለደ ጊዜ ከተወለደ በኋላ ። ሰብእ ጥበብ ሲል ነው ጥበብ ያላቸው ሰዎች ከወደ ምሥራቅ መጡ ገል ውስተ አፈ ንጉሥ እንዲል ። እንድም መሰግላን ይላል ጥበበኞች ሰዎች ማለት ነው ።

ሐተታ ፥ ቤቱ ልሔምን እነሣ ወእንቲኒ ቤተልሔም ብሎ የሚያመጣ ነውና ሄሮድስን እነሣ ወእዘዘ ይቅትሉ ኵሎ ሕፃናተ ዘቤተልሔም ብሎ የሚያመጣ ነውና ፥ እንድም ቤተልሔምን እነሣ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ፥ ትንቢት ወእንቲኒ ቤተልሔም ተብሎ ተነግሯል ምሳሌ ካሌብ ምድረ ርስትን ስልሎ ሲመለስ ኬብሮንን አይቶ መጥቶ ኢያሱን ኬብሮንን ስጠኝ ቀድሞ ሙሴ ሰጥቶኝ ነበር ፥ ካሥራ ሁለቱ ጉበኞች አንዱ እኔ ነበርኩ ያን ጊዜ ፵ ዘመን ሁኖኝ ነበር ፥ ዛሬም ፹ ዘመን ይሆነኛል ካንተ ጋራ መውጣት መውረድ ይቻለኛል ገና ከጉልበት ነኝ አለው ኢያሱ እስራኤልን አስመክሮ ሰጠው እሱዋን እጅ አድርጎ አዘብ የምትባል አገባ ። ከጠላቶቹ ወገን ነበረችና በሱዋ ስም አልጠራትም ፥ ቀጥሎ ከብታ የምትባል አገባ በከብታ ክብታ ተብላለች ቀጥሎ ኤፍራታ የምትባል አገባ ፥ በኤፍራታ ኤፍራታ ተብላለች ። ከሱዋ ወንድ ልጅ ወለደ በዚያ ወራት እንጀራ አገባ እገባ ብሎት ነበርና ስሙንም ልሔም አለው ኀብስት ማለት ነው ። ወእምጽኡ ልሔሞሙ እንዲል ኀብስቶሙ ሲል በልሔም ቤተልሔም ተብላለች ክብታ ማለት ቤተ ስብሐት ማለት ነው ቤት የእመቤታችን ስብሐት የጌታችን ምሳሌ ኤፍራታ ማለት ጸዋሪተ ፍሬ ማለት ነው ፤ ጸዋሪት የእመቤታችን ፍሬ የጌታችን ምሳሌ ቤተልሔም ማለት ቤተ ኀብስት ማለት ነው ቤት የእመቤታችን ልሔም የጌታችን ምሳሌ ።

ሄሮድስን እነሳ ዘመን ትውልድ የሚቆጠር በንጉሥ ነውና ። ታሪክ እስክንድር የሚባል ንጉሥ ነበረ እስክንድርያ የምትባል ቤት አግብቶ አቶርብሉስን ሕርቃሉስን ይወልዳል በሚሞትበት ጊዜ ለሚስቱ ታናሹን እንግሠሽ ታላቁን ካህን አድርገሽ ኑሪ አላት ፥ እድልቶ አይደለም ታናሹ ሕርቃሎስ ብልህ ነው ሰው ማሳደር ያውቃል ብሎ ነው እንጂ እንደ ነገራት አድርጋ ስትኖር ፥ ሄሮድስ ወደ ሐንዶፈር የእስራኤልን መንግሥት በማናቸውም ምክንያት ይፈላሰገው ነበርና ከታላቁ ከአትሮብሉስ ይልክበታል ፥ ታላቅ ባለህ ታናሽ አዋቂ ሳለህ ላዋቂ ያንገሡብህ በምን ምክንያት ነው ፥ ጦርም እንሶህ እንደሆነ ከኔ ወስደህ እሱን ገድለህ ንገሥ አለው እሱም እውነት መስሎት ጦር ተቀብሎ መጥቶ ወንድሙን ገድሎ ነገሠ ፥ የሕርቃሉስ አርስጥእሉስ የሚባል ልጅ ነበረው በጥበብም ቢሉ ተዋግቶም ቢሉ ያጐቱን ጆሮውን ቆረጠው ። እሥራኤል አካሉ የጐደለ አያነግሡም ነበርና መንግሥት በመካከል ሏ እኅታቸው ማርያ ትባላለች እሱዋን አግብቶ ነገሠ ምንም እሱ በጥበብ በተንኮል የነገሡ ቢመስለው መንግሥት ከቤቱ ይሁዳ አልመጣም ። ኢይጠፍዕ ምስፍና ወምልክና እምእባሉ ለይሁዳ እስከ አመ ይረከብ ዘጽኑሐ ሎቱ ተብሎ የተነገረው ትንቢት እንደ ተፈጸመ ለማጠየቅ በላዩ ላይ ስማያዊ ንጉሥ ተወለደ ለማለት ሄሮድስን እነማው ። እምብሔረ ጽባሕ እለ ብርሃን የሚገኝ ከምሥራቅ ነው ። ብርሀት ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል ፤ የምሥራቅ ወርቅ ጽሩይ ነው ፤ ጽሪት ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል እኒህስ ምን ይዘው መጥተዋል ቢሉ ሠለስቱ መላእክት ሦስቱን ንዋያት ወርቅ ዕጣን ከርቤ አምጥተው ለአዳም ሰጡት ፥ አዳም ንሥኢ ሕቴኪ ብሎ ለሔዋን ሰጣት ። ከዚያ ሲወርድ ሲዋረድ ክባታቸው እጅ ገብቷል ዠረደሽት የሚባል ፈላስፋ አባት ነበራቸው ፥ በቀትር ጊዜ ከነቅዓ ማይ አጠገብ ሁኖ ፍልስፍና ሲመለከት ድንግል በሰሌዳ ኮከብ ተሥላ ሕፃን ታቅፋ አየ ፈጥኖ በሰሌዳ ብርት ቀርጾ እኖረው ፥ በሚሞትበት ጊዜ እንዲህ ያለ ኮከብ ሲወጣ ባያችሁ ጊዜ ሰማያዊ ንጉሥ ይወለዳልና ወስዳችሁ ስጡ ብሏቸው ነበርና ያን ሰምተው ይዘው መጥተዋል ። እንድም ዘእምዘመዱ ለበለዓም እንጂ ይላቸዋል ፥ በለዓም ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ ያለውን ሰምተው ይዘው መጥተዋል ፥ እንድም ትሩፋን ባቢሎን ሳሉ ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምኃ ያበውኡ ነገሥተ ሳባ ወዓረብ ጋዳ ያመጽኡ እያሉ ሲጸልዩ ይሰሙ ነበርና ይህን ይዘው መጥተዋል ። እንድም ባሮክ አቴና ወርዶ ዐሥራ ሦስት ያህል ልሳን ተምሯል ያን ጊዜ ዛሬ የሀገራችሁ ንጉሥ የሚገበረውን ወርቅ ኋላ በሀገራችን ከኛ ወገን ንጉሥ ተወልዶ ይገበረዋል ብሎ ነግሯቸው ነበርና ይህንን ይዘው መጥተዋል ። እንድም ዳንኤል መቅደስ ትትሐነጽ እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ወእምዝ ትትመዘበር ያለውን ሰምተው ይዘው መጥተዋል ፥ እንድም ዳንኤልን ምንም እሱን በውነቱን ባይወዱት ነገሩን ይቀበሉት ነበርና ዛሬ የናንተ ሀገር ንጉሥ የሚገበረውን ኋላ ከኛ ወገን ንጉሥ ተወልዶ ይገበረዋል ብሎ ነግሯቸው ነበርና ይህኑ ሰምተው ይዘው መጥተዋል ለነዚህስ እንዲገለጽላቸው ያደረገ ስለምን ቢሉ ይሹት ነበርና ለፍቅሩ ይሳሱ ነበርና ፥ ክሕደት በዚህ ጸንቶ ነበርና ፥ ክሕደትም ወደጸናበት መሄድ ልማድ ነው አሁን በመዋዕለ ሰደቱ ክሕደት ወደጸናባቸው ወደ ግብጽ ሄደ ብሎ እንዲያመጣው በእሥራኤል ዘለፋ ለአሕዛብ ተስፋ ለመሆን አኛስ አንኳ ዐውቀን ስንመጣ እስካሁን ሳያውቁት ኑረው ብለው እንድም ከመ ይንሣእ ንዋየ አቡሁ እንጂ ይላል ያባቱን ገንዘብ ለመቀበል ፥ እሶር የእከዩ በዕብራውያን መዕብራውያን የእከዩ በእሦር እንዲል ነገሥተ ፋርስ ለጸብእ እንጂ ለፍቅር አይመጡም ነበርና በጌታ ልደት ፍቅር እንደ ተጀመረ ለማጠየቅ

፪ ወበጽሑ ውስተ ኢየሩሳሌም እንዘ ይብሉ አይቴ ሀሎ ዘተወልደ ንጉሠ አይሁድ ።

፪ የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት አለ እያሉ ፤ ኢየሩሳሌም ደረሱ ። ሐተታ ፤ ምነው ኮከቡ ይመራቸው አልነበረምን ቢሉ ከሰው ሲደርሱ ይሰውራቸው ነበርና ፤ ከዚህም ስም ላዕላዊ ስም ማእከላዊ ስም ታሕታዊ አለ ፤ ስም ላእላዊ ስም ታሕታዊ አልገለጠላቸውም ፤ ስም ማእከላዊ ገለጸላቸው እንጂ ስለምን ቢሉ ስም ላዕላዊ ገልጸላቸው ፤ አይቴ ሀሎ አምላክ ዘተወልደ አይቴ ሀሎ ፈጣሪ ዘተወልደ ብለው ጠይቀው ቢሆን ፤ እኒህ ሞኞች ተላሎች ሰማይንና ምድርን የማይችሉትን ማን ችሎት ተወለደ ይላሉ ባሏቸው ነበርና ። ይህንማ እንዳይሉ አሕዛብ አይደሉ እስራኤል አይደሉምን ትንቢት የተቆጠረውን ሱባኤ ያውቁ የለም ቢሉ ፤ በዚያውስ ላይ እኛ ይልቅ እናውቀውምን ባሏቸው ነበርና ስም ታሕታዊ ገልጸላቸው ፤ አይቴ ሀሎ ሕፃን ዘተወልደ ብለው ጠይቀው ቢሆን ፤ እነዚህ ሞኞች ተላሎች በአዕላፈ እሥራኤል ከቶማ እልፍ ሙቶ እልፍ ተወልዶ ያድራል ስንቱን እናውቅላቸዋለን ባሏቸው ነበርና ፤ ስም ማእከላዊ ገለጸላቸው ።

እስመ ርኢነ ኮከበ ዚአሁ በምሥራቅ ወመጻእነ ከመ ንሰግድ ሎቱ ።

በተፈጥሮ ገንዘቡ የሚሆን ፤ እንድም እምላያው የሚሆን ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና ፤ ይኸስ በቁሙ ኮከብ ነውን መልአክን ቢሉ ፤ መልአክ ነው ፤ በምን ይታወቃል ቢሉ ፤ ኮከብ በሌሊት እንጂ በመዓልት አይታይም ፤ በመዓልት በመታየቱ ፤ ኮከብ ወደ ምዕራብ ይሄዳል እንጂ ወደ መስዕ አይሄድም ፤ ወደመስዕ በመሄዱ ፤ ኮከብ መጥቆ ይሄዳል እንጂ በቆመ ብእሲ ዘቅዝቆ አይሄድም ፤ በቆመ ብእሲ ዘቅዝቆ በመሄዱ ይኸስ በሌሊት የሚታየውን በመዓልት እንዲታይ ወደ ምዕራብ የሚሄደውን ወደ መስዕ እንዲሄድ መጥቆ የሚሄደውን በቆመ ብእሲ ዘቅዝቆ እንዲሄድ የሚያደርግ እሱ ነው ብሎ በቁሙ ኮከብ ነው ፤ ስለምን በኮከብ መራቸው ቢሉ በለመዱት ለመሳብ ኮከብ ያመልኩ ነበርና ፤ ከዚያ ሁሉ ግብጻውያን ላም ያመልኩ ነበር በለመዱት ለመሳብ ላም ሠዉልኝ እንዳላቸው ።

፫ ወሰሚዖ ሄሮድስ ንጉሥ ደንገፀ ወተሀውከ

፫ ንጉሥ ያሉትን ሰምቶ ሄሮድስ ደነገጸ አዘነ፤ ሐተታ ፤ ንጉሥማ ከሆነ ንጉሥ ሳይገድል ይነግሣልን ብሎ ።

ወኵላ ኢየሩሳሌም ምስሌሁ ፤ ተሀውከት ያለበት ነው ። ከተማይቱ ከሱ ጋራ እንደ እሱ ተደረጸች ፤ ንጉሥ ሞት የፀሐይ እርበት የሁሉ ነውና እንድም ምስቱ ነገሥታት ማንቱ ቢማር በዲዳስፋሜልኩ ይባላሉ እልፍ እልፍ ሠራዊት አስከትለው መጥተዋልና ይኸን በሰማ ጊዜ ደነገጠ አዘነ ሕዝቡም ደነገጡ አዘኑ ፤ ፄዋዊ ተመላልሶባቸው ነበርና ፤ ታምረ ኢየሱስ ምስት ይላል ፤ ትርጓሜ ወንጌል ፲፮ ኣሉ ፤ አይጣላም ቢሉ አይጣላም ፤ ነገር እንደ ትርጓሜ ወንጌል ነው ፤ ዐሥራ ሁለት ሁነው ተነሥተዋል ፤ ፈለገ ኤፍራጥስ ሲደርሱ ንጉሠ ነገሥቱ ፍርቻዉር ይባላል ዘጠኙን ይዟቸው ተመልሷል በምን ምክንያት ቢሏ ከወደኋላችሁ ጦር ተነሣባችሁ ብለዋቸው ። እንድም ስንቅ አልቆባቸው ፤ እንድም ኢየሩሳሌም ጠባብ ናት ለሰፈር አትበቃም ብለዋቸው ምሥጢሩ ግን ከበረከት ልደቱ እንዳላሳተፋቸው ያጠይቃል ። በደቂቀ ነቢያት ወይትነሥኡ ፯ቱ ኖሎት ወ፰ቱ ሠራዊት ይላልሳ ቢሉ ፤ ሰባቱ ንጉሠ ነገሥትነት የደረሱ ናቸው ፤ አምስቱ ንጉሠ ነገሥትነት ያልደረሱ ናቸውና እንደ አንድ ንጉሠ ነገሥት አድርጎ ሳምኖሙ በማለት ተናገራቸው እንጂ ነገር እንደ ትርጓሜ ወንጌል ነው ።

፬ ወአስተጋብአሙ ለኵሎሙ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍተ ሕዝብ

፬ የሕዝቡን ጸሐፍትና ሊቃነ ካህናትን ሰበሰባቸው ፤ ሐተታ ፤ ሊቀ ካህናቱማ አንድ አይደለም ቢሉ ፤ ምሴና ዱማ ሁነው ተሾመው ነበርና ፤ እንድም አንዱ ሽም አንዱ የሽም ሽር ነው ፤ ጸሐፍት የሚላቸው ወተሠይሞሙ ለለነገዶሙ እንዲል ካሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ተወጽጽተው ርስት ከርስት ትውልድ ከትውልድ እንዳይፋለስ የሚጽፉ ናቸው ። ይልቁንም ክህነት ከቤተ ሌዊ መንግሥት ከቤተ ይሁዳ እንዳይወጣ የሚጽፉ ናቸው።እንድም ከነገደ ስምዖን ተወልደው ይኸን ሁሉ የሚጽፉ ናቸው ከኒህ ወግ ታሪክ አይታጣምና ብሎ ሰበሰባቸው ።

ወይቤሎሙ በአይቴ ይትወለድ ክርስቶስ ። ክርስቶስ ወዴት ይወለዳል ብሎ ጠየቃቸው

፭ ወይቤልዎ በቤተ ልሔም ዘይሁዳ ።

፭ እንደ ዛሬ ምቀኝነት አልለፋም ነበርና ቀንተው ይመልሱለታል ። የይሁዳ ዕፃ በምትሆን በቤተ ልሔም ነው አሉት ።

እስመ ከማሁ ጽሑፍ በነቢይ ፤ እንዲህ ያለ ጽሑፍ አለና ነበርና ይላል ወንጌላዊ ፤ ከነዋዌው ጠቀሰው ወበእንቲአከሙ ይጸርፉ አሕዛብ ላዕለ ስመ እግዚአብሔር እንዲል ።

፮ ወአንቲኒ ቤተ ልሔም ምድረ ኤፍራታ ኢትቴሐቲ እምነገሥተ ይሁዳ ፤ ሚክ ፭ ፣ ፪ ዮሐ ፯፥፵፪ ፮ የይሁዳ ዕፃ የምትሆኝ አንቺም ቤተ ልሔም የይሁዳ ነገሥታት ከነገሡባቸው አህጉር ብትበልጪ እንጂ አታንሺም የሚል ጽሑፍ አለና ነበርና ይላል እስመ እምኔኪ ይወጽእ ንጉሥ ዘይርእዮሙ ለሕዝብየ እሥራኤል ።

ወገኖቹ እሥራኤል ዘሥጋን የሚጠብቃቸው ንጉሥ ባንቺ ይነግሣልና ። ታሪክ ነቢዩ ሚክያስ ነው ሌላውን ሲያስተምር ውሎ ወደ ማታ በቤተ ልሔም በኩል አልፎ ሲሄድ ተፈታ ምድረ በዳ ሆና ቋያ በቅሎባት አየ ። እንዲህ እንጂ እንደሆንሽ አትቀሪም ንጉሥ ይነግሥብሻል የነጋሪት ድምፅ ይሰማብሻል ድንኳን ይተከልብሻል እሥራኤል ደጅ ይጠኑብሻል አሕዛብ ይገብሩብሻል ብሎ ትንቢት ተናግሯል ይህም እልቀረ ዘሩባቤል ነግሦባታል እሥራኤል ደጅ ጠንተውባታል የነጋሪት ድምፅ ተሰምቶባታል አሕዛብ ገብረውባታል ድንኳን ተተክሎባታል። እንደም ወገኖቹ እሥራኤል ዘነፍስን የሚጠብቃቸው ንጉሥ ክርስቶስ ባንች ይወለዳልና ዘሩባቤል እንደ ነገሠ ጌታ ተወልዶባታል፣ ድንኳን እንደ ተተከለባት የብርሃን ድንኳን ተተክሎባታል ፣ ነጋሪት እንደ ተሰማባት ቅዳሴ መላእክት ተሰምቶባታል ፣ እስራኤል ደጅ እንደ ጠኑ መቶው ነገደ መላእክት ደጅ ጠንተውባታል አሕዛብ እንደ ዝቡ ሰብአ ሰገል ገብረዋል ። አንድም አንቺ የኤፍራታ ልጅ እመቤታችን በይሁዳ ከነገሡ ነገሥታት ብትበልጭ እንጂ አታንሽም ፣ ወገኖቼ እሥራኤል ዘነፍስን የሚጠብቃቸው ንጉሥ ክርስቶስ ባንቺ ባሕርይ ይወለዳል፣ እምኔኪ ካንች ይወለዳልና።

፯ ወእምዝ ጸውኦሙ ሄሮድስ ለሰብአ ሰገል ጽሚተ ።

፯ ከዚህ በኋላ ሰብአ ሰገልን በቀይታ ጸራቸው ካህናትን ጠይቆ ባዳራሽ አውጥቶ ሰብአ ሰገልን በእልፍኝ ጠራቸው ፣ አሁን ከኛ ጠይቆ ይነግራችዋል እንዳይሉት ፣ አንድም ካህናትን በእልፍኝ አስወጥቶ ሰብአ ሰገልን በአዳራሽ አስጠራቸው ፣ ይኸም ውዳሴ ከንቱ ሽቶ ነው ። እኛስ እንኳን አውቀን ስንመጣ እሱ ከዚህ ሁኖ እስከዛሬ ሳይሰማ ከዚህ ሁኖ እስከ ዛሬ ሳይሰማ ኑሯል ይሉኛል ብሎ ።

ወተጠየቀ እምኔሆሙ መዋዕሊሁ በዘአስተርአየሙ ኮከብ። ኮከብ የታየበትን ቀን ጠየቃቸው ። አንድም ኮከቡ በታየበት ቀን የጌታን ዘመኑን ዐውቆ ተረዳው ፤ ይህን ኮከብ ካያችሁ ምን ያህል ዘመን ሁኖታል አላቸው ፣ ሁለት ዓመት ሁኖታል አሉት ፣ ለካ ያም ብላቴና ሁለት ዓመት ሁኖታል አለ !

፰ ወፈነዎሙ ኀበ ቤተልሔም

፰ ቤተልሔም ነው ብሎ ሰደዳቸው ።
ወይቤሎሙ ሐዊረከሙ ተስእሉ ጥዩቀ በእንተ ውእቱ ሕፃን ወእምከመ ረከብክምዎ ግብኡ ኀቤየ ወዜንውኒ ሄዳችሁ የብላቴናውን ነገር ጠይቃችሁ ድርሰውን ያገኛችሁት እንደሆነ በኔ በኩል ተመልሳችሁ ንገሩኝ አላቸው ።

ከመ እምጻእ አነሂ ወእስግድ ሎቱ ። እኔም መጥቼ መእሰግድለት ዘንድ ፣ ለሄሮድሳውያን ጉሕሉት ልማዳቸው ነውና እስግድ ሎቱ አለ እንጂ እቅትሎ ሲል ነው ሐተታ እንዲህማ ከማለት ተቀድሞ ሄዶ አይነግራቸውምን ቢሉ ካህናቱ ዘመዶቹ ናቸውና ልከው ያሸሹብኛል ብሎ ። ባንድ ሂዶ አይገድለውም ነበር ቢሉ ሰብአ ሰገል ይገሳግሉኛል ብሎ ፣ አይሆንም ያልኋቸው እንደሆነ አልፍ እልፍ ሠራዊት አስከትለው መጥተዋል አገባ መልስ ብሰው ይጣሉኛል ብሎ አንድም እኛ ብቻ መስሎን የሆገሩም ነገሥታት ያምኑበታልሳ ብለው የሰብአ ሰገል ሃይማኖታቸው እንዲጸናላቸው ፣ መንፈስ ቅዱስ አፉን ከፍቶ ፊቱን ጸፍቶ አናገረው ።

ወሰሚያሙ ሐሩ እምኀበ ንጉሥ ፤

ቤተልሔም ነው ያላቸውን ሰምተው ወተአዚዞሙ ይላል ፣ ወእምከመ ረከብክምዎ ግብኡ ኀቤየ ያላቸውን ሰምተው ንጉሥ ነውና ይበጅ ያድርግ ብሰው ሄዱ ።

፱ ወናሁ ኮከብ ዘርእዩ በምሥራቅ ይመርሆሙ እስከ ሶበ አብጽሖሙ ቤተልሔም ።

፱ በሥምራቅ ያዩት ኮከብ ቤተልሔም እስኪያደርሳቸው ይመራቸው ነበር ።
ወቆመ መልዕልተ በዓት ኀበ ሀሎ ሕፃን ።
ባለበት ቦታ በሰው ቁመት ልክ ዘቅዝቆ ቆመ በጣት ጠቅሶ እንደ ማሳየት ።

፲ ወርእዮሙ ኮከበ ተፈሥሑ ዓቢየ ፍሥሐ ።

፲ ኮከቡን አይተው ፈጽመው ደስ አላቸው ፣ ስልማዱ ከሰው ሲደርሱ ይሰወራቸው ከሰው ሲለዩ ይመራቸው ነበር አሁን ሲገሰጽላቸው እሱ እንጂ ቢሆን ነው ብለው ፣ አንድም ስንኳን ሁለት ዓመት ያሄዱለት ነገር ሁለት ሰዓት የሄዱለት ነገር ቢፈጸም ደስ ያሰኛልና ፤ አንድም እንዲህ መርቶ ከምን ያደርሰን ይሆን ፣ ከባሕር ያጠልቀን ከገደል ይጥለን ከጸር ያደርሰን ይሆን ብለው ነበርና ካሰቡት ቢያደርሳቸው ደስ አላቸው ፣ እንድም የሚቀድመው እለ ።

፲፩ ወበዊኦሙ ውስተ ቤት ረከብዎ ለሕፃን ምስለ ማርያም እሙ መዝ ፭፩፤ ፲

፲፩ ከቤት ገብተው ብላቴናውን ከናቱ ጋራ እይተው ፣ ከዚህ በኋላ ኮከቡን አይተው እምሳያው ሁና ቢያገኙት ፈጽሞ ደስ አላቸው ። ቤት በዓት ጎል ይላል አብነት ፣ ቤት ቢል የሴፍ እንደ ዳስ አድርጎ ጥሎ ነበርና በዓት ያለ እንደሆነ ኢዮስያስ በጨው ማሽጋ ግምብ አሠርቶ ነበርና ፣ ጨውን ሲልሱ እን ስሳት እየጋጡ አጕድጉደውት ነበርና ፣ ጎል ያለ እንደሆነ የተመቸ የእንስሳት ማደሪ ሁኖ ነበርና ።
ወወድቁ ወሰገዱ ሎቱ ።

ከፈረስ ከሰረገላ ወርደው ሰገዱለት ፤ አንድም መላ ልሰው ሰገዱለት ፤ ሐተታ ፤ እንደ ስናሩ ንጉሥ ጃን ተክል ሲደርስ ይሰግዳል ፤ የታዘዘ ብላቴና መጥቶ ተነሥ ብለውሃል ይለዋል ፤ ዳግም አልፎ ይሰግዳል ተነሥ ብለውሃል ይለዋል እንዲህ እያለ ከዚያ ሲደርስ እጅ ነሥቶ ከዙፋኑ በቀኝ አብሮ ይቀመጥ ነበር ። ወአርኀው መዛግብቲሆሙ ፤ ማጥናቸውን ከፈቱ ፤ እየራሳቸው ጭነዋል ያሉ እንደሆነ የተመቸ ፤ አንድ ነው ያሉ እንደሆነ ስደፉ ብዙ ነውና ፤ እንደ ስደፍ ነፍጥ ፤ አንድም ፈትሑ ወአርኀው ይላል ማጥናቸውን ከፈቱ ኮረጆዎቻቸውን ፈቱ ።

ወአብዑ ሎቱ አምኃ ወርቀ ከርቤ ወስሂነ ።

ወርቁን ዕጣኑን ከርቤውን ግብር አገቡለት ፤ ሐተታ ወርቅ አመጡለት ይህን የምንገብራቸው ነገሥታት ቀድሞም ፍጡራን ኋላም ኃላፍያን ናቸው አንተ ግን ቀድሞም ያልተፈጠርህ ነህ ኋላም የማታልፍ ነህ ሲሉ ፤ ዕጣን አመጡለት ይህን የምናጥናቸው ጣዖታት ቀድሞም ፍጡራን ኋላም ኃላፍያን ናቸው ። አንተ ግን ቀድሞም ያልተፈጠርህ ኋላም የማታልፍ ነህ ሲሉ ፤ ከርቤ አመጡለት ምንም ቀድሞ ያልተፈጠርህ ኋላም የማታልፍ ብትሆን በሰውነትህ መራራ ሞትን መቀበል አለብህ ሲሉ ፤ አንድም ወርቅ ጽሩይ ነው ፤ ጽሩየ ባሕርይ ነህ ሲሉ ፤ ዕጣን ምዑዝ ነው ፤ ምዑዝ ባሕርይ ነህ ሲሉ ፤ ከርቤ የተሰበረውን ይጠግናል የተለየውን አንድ ያደርጋል ፤ አንተም ከማኅበረ መላእክት የተለየ አዳምን አንድ ታደርገዋለህ ጽንዓ ነፍስ ሰጥተህ ታጸናዋለህ ሲሉ ፤ አንድም ወርቅ ጽሩይ ነው ባንተ ያመኑ ምእመናን ጽሩያን ምግባር ወሃይማኖት ናቸው ሲሉ ፤ ዕጣን ምዑዝ ነው ፤ ባንተ ያመኑ ምእመናን ምዑዛነ ምግባር ወሃይማኖት ናቸው ሲሉ ፤ ከርቤ አመጡለት በዕለተ ዓርብ ያቀምሱታልና ፤ አንድም ወርቅ የሰማዕታት ምሳሌ ነው ከመ ወርቅ በእሳት ፈተኖሙ ለሰማዕት እንዲል ዕጣን የባሕታውያን ፤ ከሩቅ እንዲሸት ባሕታውያንም በተስፋ ይኖራሉ ፤ ከርቤ የምእመናን በፍቅር አንድ ይሆናሉና ፤ ወርቅ አመጡለት ወርቅ የሃይማኖት ምሳሌ ወርቅ ጽሩይነቱም ግብዝነቱም የሚታወቅ በእሳት ሲፈተን ነው፤ የሃይማኖትም ጽሩይነቱና ግብዝነቱ የሚታወቅ መከራ ሲቀበሉበት ነውና ፤ ዕጣን የተስፋ ፤ ዕጣን ከሩቅ እንዲሸት ፤ ተስፋም ያልያዙትን እንደያዙት ያላዩትን እንዳዩት ታደርጋለችና ። አሚንሰ ትሬስዮ ለዘኢሀለወ ከመ ዘሀለወ እንዲል ፤ ከርቤ የፍቅር ያ አንድ እንዲያደርግ ፍቅርም አንድ ታደርጋለችና ሃይማኖት ፍቅር ተስፋ ገንዘቦችህ ናቸው ሲሉ ፤ ወርቅ ዕጣን ከርቤ ገበሩለት ፤ አንድም ወርቅ የመላእክት ዕጣን የደቂቀ አዳም ከርቤ የካልዕ ፍጥረት፤ ከመ ለስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሰግድ ኵሉ ብርክ ዘውስተ ሰማይ ወዘውስተ ምድር ወዘታሕተ ምድር እንዲል ፤ መላእክት ደቂቀ አዳም ካልዕ ፍጥረት ገንዘቦችህ ናቸው ሲሉ ወርቅ ዕጣን ከርቤ አመጡለት ይህስ ከወዴት የመጣ ነው ቢሉ ሦስቱ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤል ቅዱስ ሩፋኤል ወርቅ ዕጣን ከርቤ አምጥተው ለአዳም ሰጡት ፤ አዳም ንሥኢ ሕጼኪ ብሎ ለሔዋን ሰጣት ሔዋን ለሴት ሰጠችው ከሴት ሲወርድ ሲዋረድ ከኖኅ ደርሷል ። ኖኅ ከመርከብ ሲገባ ይዞት ገብቷል ሲወጣም ይዞት ወጥቷል በሚሞትበት ጊዜ ሴምን ልጄን ከወንድምህ ከካም ወገን ደግ ልጅ ይወለዳልና ካባት ከናቴ አስናብተህ ወርቁን ዕጣኑን ከርቤውን አጽመ አበውን አስጠብቀው ሥራት ሥራበት ብሎታል ፤ ካባት ከናቱ አስናብቶ ወርቁን ዕጣኑን ከርቤውን አሸክሞ ሲሄድ ወንድሞቹ ያሬድና ካም ተከተሉት እናንተ አልታዘዛችሁም የታዘዝን እኛ ነን ተመለሱ አላቸው ተመለሱ ፤ መልአክ ተገልጾ እየመራቸው ሄዱ ዱዳሌም ሲደርሱ ጐድጓዳ ቦታ አገኙ ዓጽመ አበውን ቀብሮ ሦስቱን ንዋያተ ሰጥቶ ሥራት ይሠራበታል ከቤት አትድረስ ዳባ ልበስ ሥጋ አትብላ ጠጅ አትጠጣ ራስክን አትላጭ ጥፍርህን አትቁረጥ በሥንዱ በወይን አስታጥቶት ብሎ ፤ እንዲህ ሁኖ ሲኖር ፤ አብርሃም ላምበቱ ነገሥት ስደም ረድቶ አራቱን ነገሥት ኮሎዶጎሞርን ድል ነሥቶ ሲመለስ ጆስ ቢሰው በመዋዕልየኑ ተፌኑ ቃለክ ወሚመ ታርእየኒሁ ኪያሃ ዕለተ እው አልቦ አለው ፤ እሱንስ ኢታየውም ምሳሌውን ታያለህና ሑር ዕድዎ ለዮርዳኖስ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ አለው ዮርዳኖስን ተሻግሮ ቢሄድ መልከ ጼዴቅ ኅብስተ በረከት ጽዋዓ አኰቴት ይዞ ተቀብሎታል ፤ መልከ ጼዴቅ የቀሳውስት አብርሃም የምእመናን ኅብስቱ የሥጋው ጽዋዕ የደሙ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ። በዚህ ጊዜ መልከ ጼዴቅ ወርቁን ዕጣኑን ከርቤውን ለአብርሃም ሰጠው ከአብርሃም ለይስሐቅ ከይስሐቅ ለያዕቆብ ደርሰዋል ያዕቆብ ወደግብጽ ሲወርድ ይዞት ወርዷል ሲወጣም ይዞት ወጥቷል ፤ ከያዕቆብ ሲወርድ ሲዋረድ ከዕሤይ ደርሰዋል ፤ ከዕሤይ ለዳዊት ከዳዊት ለሰሎሞን ከሰሎሞን ለሮብዓም ደርሰዋል ፤ በሮብዓም ጊዜ መንግሥት ከሁለት ተከፈለ ፤ ኢዮርብዓም ወልደ ናባጥ ባሥሩ ነገድ በሰማርያ ፤ ሮብዓም በሁለቱ ነገድ በኢየሩሳሌም ነገሡ ሁለቱ ቢጣሉ ሱስቀም ንጉሠ ግብጽ ለኢዮርብዓም ረዳት ሁኖ መጥቶ ሮብዓምን ወግቶ ግብጽ ይዞት ወርዷል ፤ ይህም ብቻ አይደለ ፤ ሰሎሞን ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሲገባ ብላቴኖቹ ይዘው የሚከተሉት ሦስት መቶ የወርቅ ጋሻ ሦስት መቶ የወርቅ ጦር የወርቅ ሾተል አሠርቶ ነበር ይህን ሁሉ አውርዶታል ፤ ከግብጽ ባቢሎን እንደምን ይወርዳል ቢሉ ናቡከደነጾር

ፈርዖን ኒካዑን ገድሎ ሦስት ዓመት ባቢሎን በግብጽ አለኝቶ ሲሄድ ከግብጽ ባቢሎን ይዞት ወርዷል ፤ ከዚያ አግኝተው ይዘው መጥተዋል ፡ ሲረዳውስ መጥቶ አይወስድበትም አሕዛብ የሰው ከብት ናቂዎች ናቸውና ብሎ ሮብዓምን ወጉት ሌኢያቄብዓም ሰጥቶት ይሄዳል ። ኢያቄብዓም ከኢየሩሳሌም በግብጽ ይዞት ወርዷል፤ ስልምናሶር ዐሥሩን ነገድ በማረከ ጊዜ ፋርስ ባቢሎን ይዞት ወርደዋል ከዚያ አግኝተው ይዘው መጥተዋል ። አንድም አሜስያስ በሁለቱ ነገድ በኢየሩሳሌም ዮአስ ባሥሩ ነገድ በሰማርያ ነግሠው አሜስያስ ንጉሠ ኤዶምያስን ወግቶ ሲመለስ ኃይል ቢሰማው ነዓ ንትረዓይ ገጸ በገጽ ብሎ በዮአስ ላከበት ። እሱም እስመሁ ሞዕከሙ ለኤዶምያስ ተዘግረኑ ልብከ ፤ ኢቃኒ ዘውስተ ዕፅ ለአከት ኀበ ዕፀወ ቄድሮስ እንዘ ትብል ሀብ ወለትከ ለወልድየ ፤ ወመጽኡ ዓራዊተ ገዳም ወኬድዋ ለዒቃኒ ብሎ ገሥግሦ ሄዶ ገጠመው ድል አድርጎታል በአንቀጸ ኤፍሬም አራት መቶ ክንድ አደባባይ አለ በዚያ አስገትቶታል ነገሥተ እሥራኤል ኃያላን ነን ነገሥተ ይሁዳ ድኩማን ናቸው ሲል ፤ በዚህ ጊዜ ከኢየሩሳሌም ሰማርያ አውርዶታል ፤ ከሰማርያ ስልምናሶር ዓሥሩን ነገድ በማረከ ጊዜ ፋርስ አውርዶታል ፤ ከዚያ አግኝተው ይዘው መጥተዋል ፤ ይህማ እንደይሆን ዘእንበለ ያእምር ሕፃን ሰምየ አቡሁ ወእሙ ይነሥእ ኃይለ ደማስቆ ወምህርካ ሶርያ ይት ካሬል ይላልሳ ቢሉ ወርቁ እንጂ ብዙ ነው ከዚያም ከዚያም ደርሷል ፤ አንድም አሳ በሁለቱ ነገድ ፤ በአሰ በዓሥሩ ነገድ ነግሠው ሳሉ የአሳ ፤ ራማ የምትባል መውጫ መግቢያ ነበረችው ፤ ባአሰ ሄዶ ቀጸረበት በዚህ አዝኖ ሳለ በዚህን ታዝናለህ ከወልደ አዴር ጋራ ሲወጋህ ተማምሎብሃል አሉት ኀድግአ ኪዳኖ ዘተካየድከ ምስለ በአሰ ብሎ ከቤተ እግዚአብሔር ዕቃቤት ከቤተ መንግሥት ዕቃቤት የተገኘውን ወርቅ ጨምሮ ለወልደ አዴር ወልደ ጤዲርማን ወልደ አዚን ወልደ አዛሄል ንጉሠ ሶርያ ይሰድለታል በዚህ ጊዜ ሶርያ ይወርዳል ፤ አንድም ኢዮአስ በሁለቱ ነገድ ነግሦ ሳለ አዛሄል ሰባት ያህል አኅጉር ወግቶ መጥቶ ከዳር ሰፍሮ ገብር አለው ። እቱእ እግዚእየ ዘአጸርከኒ እፀውር ብሎ ከቤተ እግዚአብሔር ዕቃቤት ከቤተ መንግሥት ዕቃቤት የተገኘውን ወርቅ ሰዶለታል ሶርያ ይወርዳል ፤ ከሶርያ ፋርስ ባቢሎን እንደምን ይወርዳል ቢሉ ቴልጌል ቴልፌልሶር በፋርስ ረዓሶን በሶርያ ፋቁሄ ወልደ ሮሜልዩ በሰማርያ አካዝ በኢየሩሳሌም ነግሠዋል በሶርያና በሰማርያ መካከል ራማት ዘገለዓድ የምትባል አገር አለች የሶርያው ሲበረታ ወደሶርያ የሰማርያው ሲበረታ ወደ ሰማርያ የምትገዛ እንደ ዋግ ያለች ናት ዋግ የትግሬው ሲበረታ ወደ ትግሬ የበጌምድሩ ሲበረታ ወደ በጌምድር ትገዛ እንደ ነበረ በዚህ ጊዜ ፋቁሄ እጅ ነበረች ። እሱም ይህችን አገር ላንተ እሰጥሃለሁ ላባቶቼ ሲገዙ የነበሩ ሁለቱ ነገድ አምፀውብኛልና እነዚያን አስገዛኝ ብሎ ከረዓሶን ላከበት በዚህ ተማምለው ሁለቱ አንድ ሁነው ወደ ኢየሩሳሌም ዘመቱ ። ወሶበ ሰምዓ ዘንተ ቤተ ዳዊት ደንገፀት ነፍሱ ወነፍሰ ኵሉ ሕዝቡ እንዲል ። አካዝ ይህን ሰምቶ ገብርከኒ ወወልድከ ፤ በግድ ባሪያህ በፈቃድ ልጅህ ነኝና ፤ እርዳኝ ብሎ ከቴልጌልቴልፌልሶር ዘንድ ላከበት እሱም ከተት ሥራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ ዘመተ ፤ ሶርያ ሲደርስ ይህች አገር የማናት ብሎ ጠየቀ የረአሶን አሉት ። እሱ ወዴት ሄዷል አለ አካዝን ሊወጋ ኢየሩሳሌም ሄዷል አሉት የአካዝን ብላቴና ጥሩ ብሎ አስጠርቶ ጌታህ እርዳኝ ብሎ የላከብኝ ወዴት ድረስ ነው አለው ። ኢየሩሳሌም ድረስ አለው ። ልጅ እንጂ ቢሆን የጦር መላ ባያውቅ ነው ብሎ ተኩስ ዝረፍ አለ ፤ የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንዲሉ ፤ የሰው አገር እንወጋለን ብላችሁ አገራችሁ ተወጋላችሁ አሏቸው ፤ ተመልሰው ገጠሙት ረዓሶን በፊት ተመቶ ከዚያው ሙቷል ፤ ፋቁሄ ተመቶ ከገፉ ይሞታል ፤ በዚህ ጊዜ ቴልጌቴልፌሶር ከሶርያ ፋርስ አውርዶታል ። ከዚያ አግኝተው ይዘው መጥተዋል አምጥተው ለእመቤታችን ሰጧት ፤ እመቤታችንም ተቀብላ ከፍላ ለነዳያን መጽውታለች ለቅዱስ ጴጥሮስ ሰጥታዋለች ቅዱስ ጴጥሮስም ከፍሎ ለነዳያን መጽውቶለት ለቀሌምንጦስ ሰጥቶታል ቀሌምንጦስ ከፍሎ ለነዳያን መጽውቶለት ከሰምንቱ መጻሕፍት ጋራ በአንቀጸ ሮም ቀብሮታል ፤ እነዚህስ ምን ጊዜ ተነሥተው ምን ጊዜ ደርሰዋል ቢሉ ለልደት ሁለት ዓመት ሲቀረው ተነሥተው የልደት ለት ደርሰዋል ይህ በምን ይታወቃል ቢሉ ኤጲፋንዮስ ዮም ተወልደ ይላልና ፤ ይህማ እንዳይሆን እመቤታችን ስብአ ሰገልን ሸኝታ አልዋለችም አላደረችም ወዲያው መንገድ ጀመረች ይላል በሰምንት ቀን ቤተ ግዝረት መግባት ባርባ ቀን ዕጕለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዞ ቤተ መቅደስ መግባት ይቀር የለም ቢሉ አይቀርም ። ቄሣር በግብር ምክንያት አስጠርቶት ሮም ሁለት ዓመት ኑሮ ይመለሣል ከዚያ በኋላ ነገሩን ያነሳዋል አንድም መንፈስ ቅዱስ ሁለት ዓመት ነገሩን አዘንግቶት ከዚህ በኋላ ያነሣዋል ። አንድም የልደት ዕለት ተነሥተው በሁለት ዓመት ደርሰዋል ወሠሊጦሙ ግብሮሙ አተው ሀገሮሙ ናዝሬት ይላል ፤ ወዴት አግኝተው ይሰጧታል ቢሉ በእድ ባረሊባኖስ ሳለች ባመት ባመት ለገቢረ በዓል ትወጣ ነበርና ከዚያ አግኝተው ይሰጧታል ፤ ኤጲፋንዮስ ዮም ተወልደ ይላልሳ ቢሉ እንጂ ዛሬ ደብተራ ባመት ባመት ዮም ተወልደ እንዲል ።

ወርቅ ያመጣ የሴም ወገን ነው መንግሥት ከሴም ወገን ነውና ፤ ዕጣን ያመጣ የያፌት ወገን ነው ካህናት ከያፌት ወገን ይበዛሉና ፤ ከርቤ ያመጣ የካም ወገን ነው ፤ ምእመናን ከካም ወገን ይበዛሉና ፤ ወርቅ ያመጣ የኻያ ዓመት ነው ፤ መንግሥት ከዚህ በላይ በ፴ ዘመን ይገባል ለማለት ፤ ዕጣን ያመጣ ያርባ ዘመን ነው መንፈሳዊ ሹመት ከዚህ በላይ ባምሳ ዘመን ይገባል ለማለት ፤ ከርቤ ያመጣ የ፷ ዘመን ነው ከዚህ በላይ ሞት ያጠራጥራልና ፤ ለነዚህም ለሕፃኑ በአምሳለ ሕፃን ለወሬዛው በአምሳለ ወሬዛ፤ ለአረጋዊው በአምሳለ አረጋዊ ታይቷቸዋል ወጥተው ሲሄዱ አንዱ መልካም ብላቴና አለ ፤ መልካም ጐልማሳ እንጂ ፤ መልካም አረጋዊ እንጂ ተባብለው ተመልሰው ቢገቡ በአምሳለ ሕፃን ለታየው በአምሳለ ወሬዛ በአምሳለ ወሬዛ ለታየው በአምሳለ አረጋዊ በአምሳለ አረጋዊ ለታየው በአምሳለ ሕፃን ታይቷቸዋል ። ከዚህ በኋላ ወጥተው ነገር እንዳንተ መልካም ብላቴና አለው ፤ እንዳንተ መልካም ጐልማሳ እንጂ እንዳንተ መልካም አረጋዊ እንጂ ተባብለዋል። መልአኩ እንደሁላችሁም ነው አትጣሉ አላቸው ፤ ማየትንስ መስማት አያስረዳውም ብለው ተመልሰው ቢገቡ በአምሳለ ሕፃን ለታየው በአምሳለ አረጋዊ በአምሳለ አረጋዊ ለታየው በአምሳለ ወሬዛ በአምሳለ ወሬዛ ለታየው በአምሳለ ሕፃን ታይቷቸው ለሁሉም ሦስት ሦስት መልክ ደርሷቸው ፍጹም አምላክነቱን በዚህ ተረድተው ሄደዋል ፤ እነዚህስ ክብር አላቸው ቢሉ የላቸውም ፤ ዕድግት በለዓምን እብነ ሆሣዕናን እንዳናገረ የታምራት ነው ፤ ይህማ እንዳይሆን አመቦ ዘአክበረ ልደተ እግዚእ ይከውን ክብሩ ምስለ ሰብአ ሰገል ይላልና ብሎ ክብር ያላቸው ናቸው ይህም ሲታወቅ ወአስነቀቶሙ ኅብስተ ሰንም ይላል አመቤታችን ሐሪጸ ሰንም ስንቅ ሰጥታ ሰደደቻቸው እልፍ እልፍ ሠራዊት እየተመገበለት ባያልቅ አገራቸው ሲደርሱ ደግን ነገር ከከተማ ፤ ይዞ መግባት አይገባም ብለው ከከተማ በአፍአ ትተውት ገቡ ፤ ደርሳችሁ መጣችሁን አሏቸው ፤ አዎን አሉ ፤ ምን ምልክት አላችሁ አሏቸው፤ እነሱም ምልክታቸውን እንዲህ ብለው ተናገሩ ሁለት ዓመት የሄድነውን በ፴ ቀን ገባን እናቱ ስንቅ ሰጥታን ይህ ሁሉ ሠራዊት እየተመገበው ባያልቅ ክቡር ነገር ነውና ከከተማ ይዞ መግባት አይገባም ብለን በአፍአ ትተነው መጥተናል አሏቸው ።

እስኪ አሳዩን አሏቸው ፤ ቢሄዱ ሲጤስ ሲነድ ተገኝቷል ። ከዚህ የተነሣ በእሳት እንጂ አምልኩ ሲሉን ነው ብለው እሳት የሚያመልኩ ሁነዋል ። ናትናኤል ሀገረ ስብከቱ ከዚያ ነውና ፤ ይኸስ የታምራት ነው ሰማዩን ምድሩን ባሕሩን የብሱን በፈጠረ በእግዚአብሔር እመኑ ብሎ አስተምሮ አሳምኖ አጥምቋቸዋልና ክብር ያላቸው ናቸው ፤

፲፪ ወነገሮሙ በሕልም ከመ ኢይግብኡ ኀበ ሄሮድስ ።

፲፪ በሄሮድስ በኩል እንዳይመለሱ በራእይ ነገራቸው ፤ ከነገ ከሠልስት ይመጣሉ ሲል እመቤታችን መንገድ እንድትገፉ ሃይማኖት እንዲሰፉ በመጡበት የተመለሱ እንደ ሆነ ሃይማኖት ይጸናል እንጂ ፤ አይሰፋም ባልመጡበት ቢመለሱ ግን ያልሰማው እየሰማ ይሰፋልና ፤ አንድ መንገድ እንዲቀርባቸው ሁለት ዓመት የመጡትን በ፴ ቀን ገቡ የሚል ነውና ።

ወእንተ ካልዕ ፍኖት ገብኡ ወአተዉ ብሐሮሙ በሌላ ጎዳና በሌላ ኃይለ ቃል በሌላ ሃይማኖት ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ገቡ ። በሌላ ጎዳና ሁለት ዓመት የሄዱትን በ፴ ቀን ገብተዋል ፤ በሌላ ኃይለ ቃል አይቴ ሀሎ እያሉ መጥተው ነበር ። ረከብናሁ እያሉ ተመልሰዋል በሌላ ሃይማኖት ንጉሥ እያሉ መጥተው ነበር አምላክ እያሉ ተመልሰዋል ። በከመ ጉየ ውስተ ምድረ ግብጽ

፲፫ ወእምድኅረ ኃለፉ እሉ ናሁ መልአከ እግዚአብሔር አስተርአዮ በሕልም ለዮሴፍ ።

ወእንተ ካልዕፍኖት ገብኡወአተው ብሐሮሙ ብሎ ነበርና ፤

፲፫ ሰብእ ሰገል ከሄዱ በኋላ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ነገረው ፤ ሳሉ አለመንገሩ ከሄዱ በኋላ መንገሩ ስለምን ነው ቢሉ፤ ሰብአ ሰገል ሳሉ ነግሮት ቢሆን ሲሰደድ አይተው አምላክነቱን በተጠራጠሩ ነበርና ፤ አንድም ካልቀረስ ይዘነው እንሂድ ባሉ ነበርና ። ይዘውትም እንዳይሄዱ የጌታ ስደቱ ወደ ግብጽ ነው እንጂ ፤ ወደ ባቢሎን አይደለምና ። እንዘ ይብል ተንሥእ ወንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወጕየይ ውስተ ምድረ ግብጽ ። ተነሥተህ እናቱን ብላቴናውን ይዘህ ወደ ግብጽ ሂድ ብሎ ነገረው ሐተታ ፤ ሕፃነ ወእሞ አለ ሕፃን ብሎ እሞን ቢተው ብላቴናውን አለኝ እንጂ እናቱን አለኝ ባለ ነበርና እም ብሎ ሕፃን ባይል እናቱን አለኝ እንጂ ብላቴናውን አለኝ ባለ ነበርና ሕፃነ ወእሞ አለ፤ አንድም ሰይጣን የሆነ እንደሆነ አመልክቶ ይቶዋል ለመልአክ ግን አካቶ መናገር ልማድ ነውና ሕፃነ ወእሞ አለ ። ወሀሉ ሀየ እስከ እመ እነግረከ ተመለስ ብየ እስክነግርህ ከዚያ ኑር አለው ። እስመ ሀለዎ ለሄሮድስ ይኅሥሦ ለሕፃን ከመ ይቅትሎ ። ሄሮድስ ብላቴናውን ሊገድለው ይሻው ዘንድ አለውና ።

፲፬ ወተንሥአ ነሥአ ሕፃነ ወእሞ በሌሊት ወሖረ ውስተ ብሔረ ግብጽ ።

፲፬ ተንሥኦ ብላቴናውን እናቱን ይዞ በሌሊት ወደ ግብጽ ሄደ ኵብላይ ልማዱ መንገዱ ሌሊት ነውና አንድም ወዲያው እንደነገረው ሳያንተላክስ ሄደ ቢል ሖረ በሌሊት አለ ፤

፲፭ ወነበረ ህየ እስከ አመ ሞቱ ለሄሮድስ ። ሆሴዕ ፤ ፲፩ ፤ ፩ ።

፲፭ ሄሮድስ እስኪሞት ድረስ ፫ ዓመት ከመ ንፈቅ በግብጽ ኖረ ።

ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ እምኀበ እግዚአብሔር በነቢይ እንዘ ይብል እምግብጽ ጸዋዕክዎ ለወልድየ፤ እግዚአብሔር በነቢይ አድሮ ነቢይ ከእግዚአብሔር ተገልጾለት በነቢዩ ቃል ልጄን ከግብጽ ጠራሁት ተብሎ የተነገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ። ሐተታ ይህማ መውጣቱን ያስረዳል እንጂ መውረዱን ያስረዳልን ቢሉ ካልወረደ መውጣትን አለ አንድም እም ቅሉ ወደ ሲሆን ነው ፤ ተጸውዑ እምቱዎፍ ሎብ ጽውዓን እምሰማይ እንዲል ልጄን ወደ ግብጽ ጠራሁት ተብሎ የተነገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ወደ ግብጽ ያደረው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊደርስ ሊፈጸም ፤ ትንቢት ናሁ እወዲ እዴየ ውስተ ምድረ ግብጽ ፤ ወትክውን አሐቲ ሀገር ምሥዋዕ ለእግዚአብሔር ይላል ደብረ ቍስቋምም እስከ ንድርያም ቢሉ ፤ ወይወርድ እግዚእነ ውስተ ምድረ ግብጽ እንዘ ይጼዓን ዲበ ደመና ቀሊል ፤ እምግብጽ ጸዋዕክዎ ለወልድየ ተብሎ ተነግሯል ፤ ይህማ የተነገረ ለያዕቆብ አይደለም ቢሉ ለጊዜው ለያዕቆብ ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ ነውና ፤ ነቢየ ያንሥእ ለክሙ እምአኀዊክሙ ያለው ለኢያሱ ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ እንደሆነ ፤ምሳሌም አባቶቹ ወደ ግብጽ ተበደዋል ትንቢቱን አውቆ አናግሯል ። ምሳሌውንም እንጂ ባወቀ አስመስሏል ፍጻሜው እንደምነው ቢሉ ግብጽ ታቀርበዋለችና ይሹታልና ለፍቅሩ ይሳሳሉና ፤ ክህደት በነዚህ ጸንቶ ነበርና ፤ ወደ ጸናበትም መሄድ ልማድ ነው ። አሁን በመዋዕለ ስብከቱ ደዌ ወደ ጸናባቸው ወደ ጌርጌሴኖን ሄደ ብሎ እንዲያመጣው ፤ አንድም ገዳማተ ግብጽን ለመባረክ ደጋጉ ገዳማት እንቢሐት እነ አስቄጥስ ከዚያ አሉና። እንድም መልኩን አይተው የሚያምኑ አሉና ። ወተበሀሳ እዋልደ ሴሐት ንዑ ንርአዮ ለወልደ መንከራት እንዲል ፤ አንድም ኪዳነ መልከ ጼዴቅን ለመፈጸም ዘመዶቼን ማርልኝ ቢለው ልጄን በሥጋ ሰድጄ እምርልሃለሁ ብሎት ነበርና ። አንድም ሃይማኖት ከሁሉ ሲጠፋ በግብጽ አይጠፋምና ፤ እስከ ምጽአት ድረስ ወልድ ዋሀድ ስትል ትኖራለችና ፤ በዚያውስ ላይ መሰደዱ ስለምነው ፤ ቢሉ እንዳይሞት ጊዜው አልደረሰምና ከዚያ ባለ ድኖም ቢሆን ምትሐት ነው ባሉ ነበርና ፤ አንድም አዳም ከዚህ ዓለም እፍአ ከምትሆን ገነት ተሰዶ ነበርና ለዚያ እንዴ ካሳ ለማጠየቅ ፤ አንድም ለሰማዕታት ስደትን ለመባረክ ሰማዕትነት ብቻ በጽኑት በስለት አይደለም ። አገርንም ጥሎ መሰደድ ሰማዕትነት ነውና ። አንድም ጕየተ ሕፃን አጕየዮ ለዲያብሎስ እንዲል ። አጋንንትን ከሰው ልቡና አስወጥቶ ለመስደድ ። በእንተ ሚጠት እምነ ግብጽ ።

፲፮ ወሶበ ርእየ ሄሮድስ ከመ ተሳለቁ ላዕሌሁ ሰብአ ሰገል ተምዓ ጥቀ ።

፲፮ ሄሮድስ እንደዘበቱበት ባየ ጊዜ ማለት ባንተ በኩል እንመለሳለን ብለው በሌላ ጎዳና እንደሄዱ በሰማ ጊዜ ፈጽሞ ተበሳጨ ፤ በማን ይበሳጫል ቢሉ ብስጩ ልማዱ ባልጋው በመከዳው በቤተ ሰቡ የጨለማ ገልማጭ እንዲሉ ።
ወአዘዘ ሐራሁ ወፈነወ ይቅትሉ ኵሎ ሕፃናተ ዘቤተልሔም ወዘኵሉ አድያሚሃ ።
በቤተልሔም ባውራጃዋ ያሉ ሕፃናትን ሁሉ ግደሉ ብሎ አዝዞ ሰደደ ። ዘ፪ኤ ዓመት ፤ ወዘይንእስሂ እምኔሁ ።
ዓመት ከመንፈቅ ፤ ዓመት የሆነውንም ፤
በከመ ሐሳበ መዋዕል ዘተጠየቀ እምኀበ ሰብአ ሰገል፤
ከሰብአ ሰገል ጠይቆ በተረዳው ዘመን ልክ ፤

፲፯ አሜሃ ተፈጸመ ዘተብህለ በኤርምያስ ነቢይ እንዘ ይብል

፲፰ ቃል ተሰምዓ በራማ ።

ያን ጊዜ ኤርምያስ ቃል በራማ ተሰማ ብሎ የተናገረው ትንቢት ደረሰ ተፈጸመ ይደርስ ይፈጸም ዘንድ አዘዘ ፤ ራማ በቁሙ ሰማይ አንድም ከፍ ባለ ቦታ ፤ አንድም በመላእክት ዘንድ ፤ አንድም በእግዚአብሔር ዘንድ፤ ብካይ፤ የልጆቻቸው ከናቶቻቸው ሲለዩዋቸው ።

ወሰቆቃው ፤
የናቶቻቸው ፤
ወገዓር ፤

የልጆቹ ጠምዘው ሲያርዷቸው
ወሕማም ብዙኀ ይላል ፱ ወር ካምስት ቀን የፀነሰ ማሕፀን አይችልምና ፤

፲፰ ራሔል እንዘ ትበኪ በእንተ ውሉዳ ኤር ፴፩ ፤ ፲፭ ።

፲፰ ራሔል ለልጆቿ ስታለቅስ ተሰማ ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ አዘዘ ። አንድም ደረሰ ተፈጸመ ።

ሐተታ ልያን አሳነሣ ራሔል አለ ምነው ቢሉ የልያ ዕዳዋ ነው ጌታ ከሷ ወገን ተወልዷልና የራሔል ግን ያለዕዳዋ ነው ጌታ ከሷ ወገን አይወለድምና አንድም የልያ በርኅቀት ሀገር

ፀብዛት ድንውሏታል የራሄል ግን በማነስ በቅርብ ኤልተውላታልና ። እንድም በራሄል ልያን መናገር ነው ፤ አንድም እናታችን ራሄል ኑራልን መከራችንን አይታ አልቅሳልን ብለው ባላለቀሱ ፤ እንድም እንድናለን መስኟቸው ከመቃብረ ራሄል ገቡተዋል ከዚያ እየገቡ ፈጅተዋቸዋልና እንድም በራሄል ሁሉን መናገር ነው ይህማ እከፍሎ ውስተ ያዕቆብ ወእዘርዎ ውስተ እሥራኤል እንዲል ፤ ሁሉን በሚገናኝ በያዕቆብ ባልተናገረውም ነበር ቢሉ ፣ መንድ ልጅ ለፈረስ ሴት ልጅ ለበርኖስ ከደረሱ በኋላ የሞቱ እንደሆነ ኃዘን ባባት ይጸናል በሕፃንነት የሞቱ እንደሆነ ግን ኃዘን በእናት ይጸናልና በሚጸናው ተናገረ ። እንድም ግፍ ለግፍ ሲያነጻጽር የቀደመችቱ ራሄል የምትባል ሴት ባሏ ርቤልም ስምእንም ይባባል ባሏ ሙቶ በባሏ ሥፍራ ኖራ እርገጭ ብልዋት ስትረግጥ መንታ ፀንሳ ኑራ ወጥተው ወጥተው ወደቁ ደንግጣ ቀመች የሰው ሥጋ ያጸናዋል እንጂ ምን ይለዋል እርገጭ አሏት አሁሉኑ በዙ ዕሚይ አምላክ እሥራኤል ብላ ዕንባዋን በእጅዋ ተቀብላ ወደ ላይ ረጭተዋለች ፤ ዕገዕኩ ገዓርሙ ለሕዝብየ ወወረድኩ ከመ አድኅኖሙ ያሰኘው ይህ ነው ። እንድም ራሄል መንግሥተ ሰማይ የሚገባባት አጥታ ታዝናለች ታለቅሳለች ።

ወዓበየት ተናዝዞ ወነጊሬ ላሀ ራሄል ልቅሶ መተውን መጽናናትን እምቢ አለች ፤ ግፉ ያሳዝናልና የጸር ሞት ነውና ኀዘን በየደጁ ሁኑአልና ።

እስመ ኢኮንዋ ውሉዳ ውሉደ ልጆቹአ ልጆች አልሆኑአትምና ሙተዋልና ማለት ነው ። እንድም እስመ ኢኮኑ ውሉደ ፤ ልጆቹ አይደሉምና የተውሶ ናቸውና ።
ወኢህለው ።

በሕይወተ ሥጋም የሉምና ፤ ሐተታ ፤ እነዚህንስ እንደምን አድርጎ ይሰበስባቸዋል ፣ ቢሉ ቄሣር ሕፃናትን ሰብስበህ ልብስ ምግብ እየሰጠህ በማር በወተት አሳድገህ ለናት ለአባታቸው ርስት ጉልት እየሰጠህ ጭፍራ ሥራልኝ ብሎኛል ብሎ ፀዋጅ ነገረ ፤ ያላት ልጅዋን የሌላት ልብስ ምግብ ልቀበልበት ብላ እየተዋሰች ይዛ ሂዳለች እንዲህ አድርጎ ሰብስቦ ፈጅቷቸዋል ። ይህስ ዕዳው ፣ በማን ይሆናል ቢሉ በሱ ፤ በዳዊት ምክንያት ፫፻ ፹፭ ሌዋውያን ቢያልቁ ፤ ፩ሳሙ ፳፪ ፤ ፲፰ በጴጥሮስ ምክንያት ፲፮ ሰዓራት ቢያልቁ ግብረ ሐዋ ፲፪፣ ፲፱ ።

ዕዳው በሳኦል በሄሮድስ ሆነ እንጂ በዳዊት በጴጥሮስ ሆነን እሊያስ ባያውቁ ነው እሱማ እያወቀ ቢሉ ያውቃልማ ካሉ ሁሉንም ያውቃል መጠቀማቸውንም ያውቃል ፤ ለነሀሰ ክብር አላቸው ቢሉ የላቸውም ይኋል ፤ ይህማ እንዳይሆን ስንክሳር ተጽፎላቸው ታቦት ተቀርጾላቸው አብያተ ክርስቲያናት ታንጾላቸው የለም ቢሉ ሳያውቁ በሠሩት ሥራ መጠቀም እንደሌለ ለማጠየቅ ነው እንጂ ክብር አላቸው

፲፱ ወመዊቶ ሄሮድስ ናሁ መልአከ እግዚአብሔር አስተርአዮ በሕልም ለዮሴፍ በብሔረ ግብጽ

፲፱ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ በግብጽ ሳለ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ለዮሴፍ በህልም ነገረው

፳ እንዘ ይብል ተንሥእ ንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወሑር ውስተ ምድረ እሥራኤል ።

፳ ተነሥተህ ብላቴናውን እናቱን ይዘህ ወደ ምድረ እሥራኤል ተመለስ ብሎ ነገረው ።
እስመ ሞቱ እለ የኃሥሥዋ ለነፍሱ ዝ ሕፃን ።
የዚህን ብላቴና ሰውነት ለጥፋት የሚሹዋት ሰዎች ሙተዋልና ፤ ኢትቅትል ነፍሰ እንዲል ፤ እንድም ነፍስ እንደነሣ ለማጠየቅ ለነፍሱ ዝ ሕፃን አለ ። ሐተታ ፤ ምነው የሞተ አንድ ሄሮድስ አይደለም ሞቱ ብሎ አበዛ ቢሉ ፤ የምክር ኃናቸው እሱ ነው እሱ ከሞተ ያነሡታልን ብሎ ፤ አንድም በሦስት ዓመት ከመንፈቅ ስንኳን በዓላውያን ከተማ በምእመናን ከተማስ እንኳ ብዙ ሰዎች ይሞታሉና ፤ እሱንም የመሰሉ ሰዎች ሙተዋልና ሞቱ አለ ።

፳፩ ወተንሥአ ነሥአ ሕፃነ ወእሞ ወቦአ ውስተ ምድረ እሥራኤል

፳፩ ተነሥቶ ብላቴናውን እናቱን ይዞ ወደ ምድረ እሥራኤል ተመለሰ ።

፳፪ ወሰሚዖ ከመ አርኬላኦስ ነግሠ ለይሁዳ ህየንተ አቡሁ ሄሮድስ ፈርሀ ሐዊረ ህየ ።

፳፪ ባባቱ በሄሮድስ ፈንታ ይሁዳን ሊመግዛት አርኬላኦስ እንደ ነገሠ ሰምቶ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ፈራ ። ሐተታ የክፉ ልጅ ክፉ አውሬ ያባቱን ክፋት ይተውናል ብሎ ፤ እንድም ልጆቻቸው የሞቱባቸው የይሁዳ ሰዎች ልጆቻችን ያለቁ ባንተ ልጅ ምክንያት አይደለም ብለው ቢጣሉኝ ብሎ ደም ፈራ ፤ ወአስተርአዮ በሕልም ፤ በሕልም ነገረው ። ወተግኅሠ ውስተ ደወለ ገሊላ ገሊላ ገባ ተገኃሠ አጋእዝትየ እንዲል ።

፳፫ ወበጺሖ ኀደረ ውስተ ብሔር እንተ ስማ ናዝሬት ፤

፳፫ ገሊላ ደርሶ ናዝሬት ገብቶ ናዝሬት በምትባል አገር ኖረ ፤ ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ በነቢይ ከመ ናዝራዊ ይሰመይ ወልድየ ።
ልጄ እንደ ናዝራዊ እንደ ሶምሶን ይባላል ተብሎ በነቢይ ቃል የተነገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ ። ሐተታ እንዲህ የሚል ወዴት አለ ቢሉ በኄኖክ ጠፍቷል በዚዮቄም እንደጠፉበት

ማግጸ ዕሎምን ታውቋል ። ይህስ እዝራ ነሥእን ወአስተጋብእን ይለዋል ብሎ ተናግሮት ሳይጸፍ የቀረ ነው ። ተናግረውት የቀረውን ማምጣት ለሐዋርያት ልማድ ነው ። ተጓቀቡ በመዋዕለ አፅራር ያለውን በከመ ይቤ ኢዮብ እንዳሉ እንደ ናዝራዊ እንደ ሶምሶን ይባላል ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ በናዝሬት ኖረ ፤ አንድም በአራቱ እስመ ናዝራዊ ሐዲስ ውእቱ ለእግዚአብሔር ያለውን እንዲህ ስውጦ እንጸበበው ፤ ይህንማ የተናገረ መልአክ አይደለም ስለምን ነቢይ አለው ቢሉ ፤ መልአክ ይሰመይ በእንተ ተልእኮቱ ወሐዋርያ ይሰመይ በእንተ ሐዊሮቱ እንዲል ፤ ከዚያ በግብሩ መልአክ እንደ አለው ከዚህም በግብሩ ነቢይ አለው ። ያውስ ቢሆን ይህ የተነገረ ለሶምሶን አይደለምን ቢሉ ፤ ለጊዜው ስሶምሶን ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ ነውና ፤ እነ እከውኖ አባሁ ወውእቱ ይከውነኒ ወልድየ ያለው ለጊዜው ለሰሎሞን ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ እንደ ሆነ ያውስ ቢሆን በምን ይመስለዋልና እንዲህ አለ ቢሉ ፤ ሶምሶን በተናቀች መንሰከ አድግ ጠላቶቹን እንዳጠፋ ጌታም አይሁድ አጋንንት መናፍቃን በናቁት ሞቱ ሞትን አጥፍቷልና ። ሶምሶን በሕይወተ ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው አሕዛብ በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉና ፤ ጌታም በሕይወተ ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው አጋንንት በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉና ። አንድም ከመ ናዝራዊ ይሰመይ ብለህ ናዝሬት ማለት ፍልጠት ክፍለት ማለት ነው ። ልጁ ልዩ ይባል ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ ። ዘተብህለ በነቢይ ስሙ ለልዑል ቅዱስ ቅዱሳን ወይትቀባዕ ቅዱስ ቅዱሳን ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ አንድም ናዝሬት ማለት ንሥርት ማለት ነው ፤ ይእቲ አሚረ ይሰምያ ለናዝሬት በስመ ኃሣር እንዲል ። ልጁ ንሡር ይባል ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ እልህን ሡር እንዲል በዓረብ ንሡር ቢል ፤ አንድም ናዝሬት ማለት አጽቀ ጽጌ ማለት ነው ልጁ አጽቀያዊ ጽጌያዊ ይባል ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ ። እሱ አንዱ ጕንድ ኖሁ ምእመናንን እንደ አዕጹቅ እንደ ጽጌያት አድርጎ ያስገኘልና ፤ ያው ግን በነቢይ ቃል ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሤይ ወየዓርግ ጽጌ እምጕንዱ ተብሎ የተነገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው ።

በእንተ ስብከቱ ዮሐንስ ።

ምዕራፍ ፫ ፤

፩ ወበውእቱ መዋዕል በጽሐ ዮሐንስ መጥምቅ እንዘ ይሰብክ በገዳመ ይሁዳ ዘዮርዳኖስ ፤

፩ ከመ ናዝራዊ ይሰመይ ወልድየ ብሎ ነበርና ናዝራዊ በተባለበት ወራት ፤ ቦአ ናዝሬተ ብሎ ነበርና ናዝሬት በገባበት ወራት ፤ ሃያ አምስቱን ዘመን እንደ ወጣን አድርጎ ወበውእቱ መዋዕል አለ በዮሐንስ አርባውን ቀን እንዳንድ ቀን አድርጎ ወእመ ሳኒታ እንዳለ ። አንድም ወተወልደ ብሎ ነበርና ሥጋ በሆነበት ወራት ። አንድም ለዮሐንስ ሠላሳ ሲመላው ለጌታ መንፈቅ ሲቀረው በዚያ ወራት የዮርዳኖስ አውራጃ በምትሆን በይሁዳ ምድረ በዳ ዮሐንስ መጥምቅ ሲያስተምር ደረሰ ፤ በገዳም አለ ቦታው ነውና አንድም በገዳም ዕንጨት በባሕ ውኃ ቆጂ አይታጣምና ፤ አንድም በገዳም ጸር ይቀላል ለወጣንያን እብነት ለመሆን በገዳም ጸር ይጸናል ለፍጹማን እብነት ለመሆን ፤ አንድም ገዳም የአይሁድ ልቡና ነው ። በገዳም እፀል ተክል እንዳይገኝ በአይሁድም ልቡና ምግባር ሃይማኖት አይገኝምና አንድም ኢሳይያስ ቃለ ዓዋዲ ዘይሰብክ በገዳም ብሎ የተናገረልኝ እኔ ነኝ ሲል ።

፪ እንዘ ይብል ንስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ፤ ማር ፩ ፡ ፪ ፡ ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፫ ።

፪ መንግሥተ ሰማያት በልጅነት ልጅነት በሃይማኖት ልትሰጥ ቀርባለችና እመኑ እያለ ሲያስተምር ደረሰ ።

፫ እስመ ዝንቱ ውእቱ ዘተብህለ በኢሳይያስ ነቢይ እንዘ ይብል ቃል ዓዋዲ ዘይሰብክ በገዳም ። ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፫ ። ማር ፡ ፩ ፡ ፫ ። ሉቃ ፡ ፫ ፣ ፬ ።

፫ ፤ በገዳም የሚያስተምር ዐዋጅ ነጋሪ ተብሎ በኢሳይያስ ቃል የተነገረለት ይህ ዮሐንስ ነውና ቃለ ዐዐዋዲ ፤ እዕዋዴ ቃል ይላል ትምህርቱን ከዚያም ከዚያም የሚያደርስ ማለት ነው ቃል ዓዋዲ ይላል ። ይህንንም ቃል ዘይኬልህ በገዳም ብሎ ሊቁ ወስዶታል ።

ወይቤል ጺሑ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ፤ የእግዚአብሔርን መንገድ ጽረጉ ። ወርቱዓ ግበሩ መጽያሕቶ ።

ጽርጊያውን የቀና አድርጉ እያለ ሲያስተምር ደረሰ ሐተታ ፤ ንጉሥ በመጣ ጊዜ ተራራው ኮረብታው ተንዶ ጕድጓዳው መልቶ ሥሩ ተነቅሎ ደንጊያው ተለቅሞ ለፈረስ ለሠረገላ እንዲመች ቀዶ ልድሉ ይቆያልና በዚያ ግሥ ተናገረው ። የእግዚአብሔር ማደሪያ ሰውነታችሁን ከኃጢአት ከጣአት ንጹሕ አድርጉ ።

፬ ወልብሱ ለዮሐንስ ኮነ እምፀጕረ ገመል ፤ ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ነገሥታት እንጂ ኪታ ሳንቃ ያልብሱኝ ብሎ ነው ትሉኝ እንደሆን ፤ ይህ ለሥጋውያን ነው ። እሱ ግን መንፈሳዊ ነውና

፭ ይህን አይሻም ፤ ዮሐንስስ የሚለብሰው የገመል ጠጕር ነበር ። ሐተታ የገመል ምን ጠጕር እላትና ቢሉ ከጋማዋ ከጅራቷ ቢፈልጉ አይታጣም

ልብሱን ሲል ወምበዴ ይጣላዋል ብላ እናቱ ያንን እምርታ አልብሳው ነበር ፤ አንድም ገመል በቀለኛ ናት አዋብቆ የመታትን እስከ ፯ እስከ ፺ ዓመት አትዘንጋም ባዋብላ ትረግጠዋለች ሥፍራ ሲመቻት ገደል ገፍታ ትጥለዋለች ። እሱም ወይወድይዎሙ ውስተ እቶነ እሳት የምትል ሕገ በቀል ወንጌልን አስተምራለሁ ሲል ። አንድም ገመል ሁለት ግብር አላት ። የሚበላና የማይበላ እንደ ላምና እንደ በሬ ምንዛን ታወጣለች እንደ ፈረስ እንደ በቅሎ ሰኮናዋ ጽፉቅ ነው ። እስመ ገመል ጽፉቅ ሰኮናሁ ወያመሰኩዕ እንዲል ። እሱም ሕገ አሕዛብ ወሕዝብ ወንጌልን አስተምራለሁ ሲል ፤ አንድምገመሉ የሚባል ዕፅ አለ ቆርጠው አድርቀው ከባሕር የጣሉት እንደ ሆነ ጭረት ይወጣዋል ያንን ታትታ አልብሳዋለች ለጊዜው ኑሮው በገዳም ነውና ልብሱን ሲል ወምበዴ እንዳይጣላው ነው ። ፍጻሜው ግን ለምእመናን አብነት ለመሆን ተርታ ልብስ ለብሳችሁ እልባሴ መስላችሁ ኑሩ ለማለት ።

ወቅናቱ ዘአዲም ውስተ ሐቌሁ ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ነገሥታት እንጂ የወርቅ ዝናር ያስታጥቁኝ ብሎ ነው ትሉኝ እንደሆነ ። ይህ ለሥጋውያን ነው ። እሱ ግን መንፈሳዊ ነውና ይኸን አይሻም ። እሱስ ወገቡን የሚታጠቅበት ዓረብ ነበር ፤ ያ ከደመ ነፍስ የተለየ እንደሆነ ፤ እሱም ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ልዩ ነኝ ሲል ፤ ይኸን አስቀድሞ ከደመ ነፍስ ይለዩታል ከወኃ ይነከሩታል ኋላ ጢጕሩን ይመልጡታል ያለፉታል ቀለም ያገቡታል ፤ ከደመ ነፍስ እንዲለዩት መከር አስተምሮ ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ይለያቸዋል ፤ ከውኃ እንደ መንከር ያጠምቃቸዋል ያስተምራቸዋል እንደ ማልፋት ምግባር ሃይማኖት ያሠራቸዋል ቀለም እንደ ማግባት ጸጋ ክብር ያሰጣቸዋል ዮሐንስ ግን እንዲህ ማድረጉ ፍትወት እንስሳዊት ሢባሕርዩ እያለች በገቢር አንዳላወረዳት ያጢይቃል ።

ወሲሳዩ አንበጣ ወመዓረ ገዳም ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ነገሥታት እንጂ ጣቦ ጋቦዶሮ ሰቅሰቆ ያብሉኝ ብሎ ነው ትሉኝ እንደ ሆነ ይህ ለሥጋውያን ነው ፤ እሱ ግን መንፈሳዊ ነውና ይህን አይሻም ምግቡም አንበጣ የሚባል ቅጠል ደቁሶ ጨው ነስንሶ ነበር ፤ አንድም አንበጣ በልሳነ እቴና ቀምሲስ ይለዋል በኛም ሰበቦት የጋጃ ማ ይባላል ። ወመዓረ ገዳም አለ ። የማጓማር ይሏል ፤ አንድም አንበጣ ይላል በቁሙ አንበጣውን ይበላው ነበር ፤ በዐረቡ እልጅራድ ይላል አንበጣ ሲል ፤ ሐተታ ፤ በዘመኑዋ እያሉ እንድታልፍ ለማጠየቅ አሪትን አይጠብቋትም ነበር። በ፫ ቀን ግዘሩ የምትለውን ኢያሱ በ፵ ዘመን ገዝሯል ። ሶምሶን ከአፈ አንበሳ መዓር አግኝቶ ተመግቧል ከመንሰከ አድግ ውኃ ጠጥቷል ። ኤልያስም በአፈ ቋዕ ሥጋ እየመጣለት ይበላ ነበር ፤ ዮሐንስም በቁሙ አንበጣውን ይበላው ነበር ። ወመዓረ ገዳም ባለው ወመዓረ ጸደና ይላል ፤ የጣዝማ ማር ፤ ይህንም ሲቁ ጽንበጣ ዘይቤ ልዕልና ስብከቱ ይእቲ ፤ መዓር ዘይቤ ጣዕመ ስብከቱ ይእቲ ብሎ ተርጕሞታል ።

፭ ወየሐውሩ ኀቤሁ ኵሎሙ ሰብአ ይሁዳ ወኢየሩሳሌም ወኵሉ አድያሚሃ ለዮርዳኖስ ።
ማር ፩ ፣ ፭ ።

በኢየሩሳሌም በይሁዳ በዮርዳኖስ አውራጃ ያሉ ሰዎች ሁሉ ከሱ ዘንድ እየሄዱ ፤

፮ ወያጠምቆሙ ለኵሎሙ በፈለገ ዮርዳኖስ እንዘ ይትአመኑ ኃጢአቲሆሙ ።

፮ ኃጢአታቸውን እየነገሩት በዮርዳኖስ ያጠምቃቸው ነበር ። እገሌ ተጠመቅ በማየ ንስሐ ከመ ትኩን ረድአ ለክርስቶስ እያለ ፤ ሐተታ ፤ ጥምቀት ከሦስት ወገን ነው ። መዝገበ ውሉድ ፍቁራን የምትባል የጌታ ጥምቀት ፤ ጥምቀተ ዮሐንስ ጥምቀተ አይሁድ ፤ ጥምቀተ አይሁድና ጥምቀተ ዮሐንስማ አንድ አይሆንም ሁሉም ልጅነት አያሰጥ ቢሉ አንድ አይደለም ከሰውነታቸው ሰውነቱ እንዲበልጥ ፤ ከጥምቀታቸውም ጥምቀቱ ይበልጣል ። አንድም ፰ ወገን ነው ፬ቱ ምሳሌ ፬ቱ እማናዊ ፤ ምሳሌ አጥመቃ ለምድር በማየ አይህ ፤ ወለኵሎሙ አበዊነ አጥመቆሙ ሙሴ በደመና ወበባሕር ፤ ወተጠምቃ አገሪሆሙ ለካህናት ያለው ፤ ጥምቀተ ዮሐንስ ፤ ይህ ምሳሌ ነው ። አራቱ አማናዊ መዝገበ ውሉድ ፍቁራን የምትባል የጌታ ጥምቀት እንብዓ ንስሐ፡ ደመ ሰማዕት ባሕረ እሳት ።

፯ ወሶበ ርእየ ብዙኀነ እሕዛበ እምፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን እንዘ ይመጽኡ ውስተ ጥምቀቱ ጽሚተ ። ሉቃ ፫ ፣ ፯ ።

፯ ከጸሐፍት ከፈሪሳውያን ወገን ብዙ ሰዎች ጻድቃን መስለው ኃጢአታቸውን ሰውረው አልባሌ መስለው ተርታ ልብስ ለብሰው የአሪትን መፍረሻ የወንጌልን መታነጫ እናያለን ብለው እሱ ወደሚያጠምቅበት ሲመጡ ባየ ጊዜ ፤ ሐተታ ፤ እሥራኤል አይደለም ስለምን እሕዛብ አላቸው ቢሉ ስለብዛታቸው ፤ እንድም በጸያፍ የገባ ግብረ አሕዛብ ይሠራሉና ፤ ባባታቸው በፋሬስ ፈሪሳውያን በሳዶቅ ሰዱቃውያን ተብለዋል ባባትም ስም መጠራት ልማድ ነው ። በዔቦር ዕብራውያን በይሁዳ አይሁድ እንደ ተባሉ ።

ወይቤሎሙ አ ትውልደ አራዊተ ምድር መኑ አመረከሙ ትጕየዩ እመቅሠፍት ወእመንሱት ዘይመጽእ ።

እናንተ የፍኝት እባብ ልጆች በነፍስ በሥጋ ከሚመጣው መከራ ትድኑ ዘንድ ማን ነገራችሁ ። እመቅሠፍት ወእመንሱት ወእመዓት ዘይመጽእ ይላል ። በጥሞስ በሐሳዌ መሢሕ በምጽዓት ከሚመጣው መከራ ትድኑ ዘንድ ማን ነገራችሁ ። ሲማሩለት እንዳልመጡ ያውቅ የለምን ቢሉ የማይጠቀም ከጉባዔው አይመጣምና እንድም የሹም ስነፍ ባይለፈልፍ እንዲሉ ፤ ንግር ወኢታርምም ብሎታልና ። አባቶቻቸው ወደው ባወጡት ስም ትውልደ አራዊተ ምድር አላቸው ። ወንድማቸውን የሴፍን ሸጠው ልብሱን አኩዶ አርዌ በልዖ ብለው ነበርና ። ትውልደ አራዊተ ምድር ያላት አርዌ ገሞራዊት ናት አፈ ማኅፀኑዋ ጠባብ ነው፥ ዘሩን ባፏ ትቀበለዋለች እባለ ዘሩን ቆርጣ ታስተረፈዋለች ። በፅንስ ጊዜ እባት ይሞታል በሚወለዱበትም ጊዜ አፈ ማኅፀኑዋ ጠባብ ነውና ሥጋዋን በልተው ሆዷን ቀደው ይወጣሉ ፥ በዚህ ጊዜ እናት ትሞታለች እኒህም እንዳባት የሚሆኑዋቸውን ነቢያትን እንደ እናት የሚሆኑዋቸው ሐዋርያትን ገድለዋልና ። ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም እንተ ትቀትሎሙ ለነቢያት ወትዌግሮሙ ለሐዋርያት እለ ተፈነው ኀቤየ ብሎ እንዲያመጣው

፰ ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሥርናየ ዘይደልወክሙ ለንስሓ ።

፰ ከእንግዲህስ ወዲህ ለማመን የሚያበቃችሁን ሥራ ሥሩ ።

፱ ወኢይምሰልክሙ ዘታመሥጡ በብሂለ ዘትብሉ አብ ብነ አብርሃም ፤ ዮሐ ፡ ፰ ፥ ፴፱ ።

፱ አብርሃምን ያህል አባት ሳለን ትውልደ አራዊተ ምድር ይለናል በማለት ትውልደ አራዊተ ምድር ከመባል የምትድኑ አይምሰላችሁ ፥ እንዲሉት ዐውቆ አመጣ እንዲሉትም ዐውቆ ማምጣት ልማድ ነው ። ብጹዓን ብጹዓን እያለ ሲያስተምር ሰምተው ኦሪትን ነቢያትን ሲያሳልፋቸው መጥቷል እንዲሉት ዐውቆ ኢይምሰልክሙ ዘመጻእኩ እስዓሮሙ ለኦሪት ወነቢያት ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ እፈጽሞሙ እንዳለ ። ወኢትሁቦ ለጻድቅከ ይርአይ ሙስና ቢላቸው ፥ ይህንማ ዳዊት የተናገረው ለራሱ አይደለም እንዲሉት ዐውቆ ታበውሁ ነሁ እ ሰብእ ንንግርከሙ ከሡተ በእንተ ዳዊት ርእሰ አበው ቀደምት ከመሂ ሞተ ወተቀብረ እንዳለ ከዚህም እንዲህ አለ ።

እብለክሙ ከመ ይክል እግዚአብሔር አምእላንቱ አዕባን አንሥኦ ውሉደ ለአብርሃም ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም ከነዚህ ከአሕዛብ ልጅ ማሥነሣት አቅሞ ውሉድ ይላል መተካት እንዲቻለው ይቻለዋል ብየ እነግራችኋለሁ ፥ አንሥኦ ውሉድ አንሥኦ ውሉደ ይላል ። እላንቱ አላቸው አሁን ያሉ በመካከል ነውና ኋላ ብሔረ ጌርጌሴን ገባ ብሎ እንዲያመጣቸው ፥ አዕባን አላቸው ደንጊያ ያመልኩሉና ፥ እንድም ይቡስ ነው ይቡሳን አእምሮ ናቸውና ፥ ቆሪር ነው ፥ ቆሪራን አእምሮ ናቸውና ፥ ክቡድ ነው ክቡዳን አእምሮ ናቸውና ።

፲ እስመ ናሁ ተሠይመ ማሕጼ ውስተ ጉንደ ዕፀው ይንበር ፤

፲ ምሳር ዓፅቁን ከግንዱ ሊለይ ተቃቷልና ። ማለት ያናንተን ልጅነት ከአብርሃም አባትነት ሊለይ ሥልጣነ እግዚአብሔር ተቃጥቷልና ኢይምሰልክሙ በብሂለ ዘትብሉ ላለው ፤ ወንጌል ሕገ አሕዛብ ወሕዝብ ሁና ተሠርታለችና ፥ እብለክሙ ከመ እግዚአብሔር ይክል አንሥኦ ውሉደ ላለው ፥ መለኮት ከሥጋ ተዋሕዷልና መንአመረክሙ ላለው ክፉውን ሕሊና ከበጎ ሕሊና ሊለይ ሥልጣነ ክህነት ተቃጥቷልና ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሠናየ ዘይደልወክሙ ለንስሐ ላለው ፥

ኵሉኬ ዕፅ ዘኢይፈሪ ፍሬ ሠናየ ይገዘምዎ ወውስተ እሳት ይወድይዎ ።

በጎ ፍሬ የማያፈራውን ዕፅ ሁሉ ይቆርጡታል በእሳት ያቃጥሉታል ፥ በኔ ትምህርት አምኖ በጎ ሥራ የማይሠራውን ሰው ሁሉ ነፍሱን ከሥጋው ይለዩታል በገሃነም ሥቃይ ያመጡበታል ።

፲፩ አንሰኬ አጠምቀክሙ በማይ ለንስሐ ፤ ማር ፩ ፰፥ ሉቃ ፫፥፲፮ ዮሐ ፩፥፳፯ ግብ ሐ፥፩፥፭። በዚህ ያልተያያዘ በሉቃስ የተያያዘ ነው ባለጸጎች መጥተው ምንተ ንግበር አሉት ፥ ዘቦ ፪ኤ ክዳናት የሀብ ፩ደ ለዘአልቦቱ ወዘሂ ቦ እክል ከማሁ ይግበር አላቸው ፥ ኃጥአን መጸብሐን መጥተው ምንተ ንግበር አሉት ። አልቦ ፍድፋዴ ዘትገብሩ እምዘተአዘዘክሙ አላቸው እንበሳ ወደቅ የወርቅ ተኩስ የግምጃው መከንጃ የሳሙን መንጃ እያሉ የሚወስዱት አሳቸውና ፥ የደል ጭፍራ መጥተው ምንተ ንግበር አሉት ፤ ኢትዓገሉ ወኢትሂዱ መነሂ አላ ንበሩ በበሲሳይክሙ አላቸው ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ክርስቶስ እንጂ ቢሆን ነው ብለዋል እኔስ ለጸጅ ቢረሴን

፲፩ ለልብስ ኀላን እንዲያጽቡለት ሰሱ ጥምቀት በሚያበቃ ጥምቀት አጠምቃችኋለሁ ሰሱ ተአምምኖ ጣውእ በሚያበቃ ተአምኖ ኃጣውእ አስተምራችኋለሁ እንጂ ክርስቶስ አይደለሁም ።

ወዘይመጽእ እምድኅሬየ ውእቱ ይጸንዕ እምኔየ ። ከኔ በኋላ የሚመጣው እሱ ከኔ አስቀድሞ የነበረው ነው አለ ። የባሕርይ አምላክ ነው ።

ዘኢይደልወኒ እጹር ዓሣዕኖ ። ጫማውን ልይዝ የማይገባኝ ። ሐተታ ፥ የንጉሥን የንግሥትን ጫማ ትበቃለህ ያላሉት ሰው አይዝምና ።

አንደዎም ዓሕርዮን ልመረምር ከማይቻለኝ ፤ እንድም ፡ እሱ ከሚያደርገው ከታምራቱ ከትሩፋቱ አንዱን ሳያደርግ ከማይቻለኝ ፡ እንድም እግዕነ መርገምን ከምእመናን ለአንዱ አርቅልት ዘንድ ከማይቻለኝ ከኔ አስቀድሞ የነበረ ነው ።

ወእቱሰ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወበእሳት ፤ እሱ ግን በጀ ብትሉ በመንፈስ ቅዱስ በጀ ባትሉ ፀዘነመ እሳት ያጠምቃችኋል ፤ ዘየነምሰ ምድር ይእቲ እንተ ኢትመልዕ ማየ እንዲል ፤እንድም በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያጠምቃችኋል ። ሐተታ ፡ መንፈስ ቅዱስን እሳት አለው ፡ እሳት ምሉእ ነው፡ መንፈስ ቅዱስም ምሉእ ነውና ፤ እሳት በምልአት ባለቡባድ ካልመቱ አይገለጽም ። መንፈስ ቅዱስም ቋንቋ ሲያናግር ምሥጢር ሲያስተረጉም እንጅ አድሮ ሳለ አይታወቅምና ፤ እሳት ከቡላዱ ሲወጣ በመጠን ነው ኋላ በዕንጨት እያቀጣጠሉ ያስፋታል መንፈስ ቅዱስም በጥምቀት ሲሰጥ በመጠን ነው። ኋላ በሥራ ያስፋታልና እሳት ጣዕምን መዓዛን ያመጻል ፡ መንፈስ ቅዱስም ጣዕመ ጸጋን መዓዛ ጸጋን ያመጣልና፡እሳት በመጠን ቢሞቁት ሕይወት ይሆናል ። ከመጠን ወጥቶ የሞቁት እንደሆነ ግን ያቃጥላል ። መንፈስ ቅዱስም በሚገባ በተጻፈው የመረመሩት እንደሆነ ሕይወት ይሆናል ፤ በማይገባ ከተጻፈው ወጥቶ የመረመሩት እንደሆነ ግን ይቀስፋልና እሳት በላኢ ለዓማፅያን ለእለ ይክህዱ ስሞ ወእሳት ማሕየዊ ለርቱዓነ ልብ ለእለ ይገብሩ ፈቃዶ እንዲል ፤ እሳት ያቀረቡለትን ሁሉ ያቃጥላል መንፈስ ቅዱስም ሕዝብ አሕዛብ የጸለዩትን ጸሎት ያቀረቡትን መሥዋዕት ይቀበላልና ፤ እሳት ወኃ ገደል ካልከለከለው ሁሉን ሳጥፉ ቢል ይቻለዋል ። መንፈስ ቅዱስም ቸርነቱ ካልከለከለው ሁሉን ሳጥፉ ቢል ይቻለዋልና እሳት ዱር ይገልጻል መንፈስ ቅዱስም ምሥጢር ይገልጻልና እሳት የበሳው መሬት ለእህል ለተክል ይመቻል ፡ መንፈስ ቅዱስም ያደረበት ሰውነት ለገድል ለትሩፋት ይመቻልና እሳት ከዛገላቸው ሳይላተፍ ሰባቱን መዓድናት ያጸራቸዋል መንፈስ ቅዱስም ከግብራቸው ሳይለተፍ ሁሉን ያነጻልና ይእቲ ታነጽሕ ወኢትረኩስ እንዲል ፤ እሳት ካንዱ ፋና አምሳ ስልሳ ፋና ቢያበሩለት ተከፍሎ የለበትም ፤ መንፈስ ቅዱስም ተከፍሎ ሳይኖርበት እስከ ምጽአት ድረስ ሲሰጥ ይኖራልና ይእቲ ትሁብ ወኢትቀብል እንዲል በእሳት ቀድሞ ሰብእ ሰዶም ሰብእ ገሞራን ከእሥራኤል አንዱን ጎብር አጥፍቶበታል ለመዓት እንጅ ለምሕረት አልተፈጠረም እንዳይሉ ለምሕረትም እንደ ተፈጠረ ለማጠየቅ ። እንድም ሽክላ ሠሪ ሠርታ ስትጨርስ ንቅ ያገኘችበት እንደሆነ እንደ ገና መልሳ ከሰክላ በውኃ ለውሳ በእሳት ታድለዋለች ። ተሐድሶም በመንፈስ ቅዱስ ነውና ፤ ዛቲ እሳት እንተ ኮነ ይትዓፀፋ አዳም እንበለ ይትዓዶ ትእዛዘ እግዚአብሔር ፈጣሪሁ ከመ ነበረ ውዓተ ጊዜ ውዕዐ በልዓ እምዕፀ ዕልወት ተዓርቀ ወኢረከበ እስከነ መጽአ አዳም ዳግማዊ ወአለ/ሁ እኑመ እግዶ ወእመንፈስ እንዲል

፲፪ ዘመሥኤ ውስተ እዴሁ ዘቦቱ ያነጽሕ ዓውደ እክሉ ።

፲፪ ፍሬውን ከገለባ የሚለይበት መንሽ በጁ ተይዞ ያለ ።

ወያስተጋብእ ሥርናዮ ውስተ መዛግብቲሁ ። ፍሬውን ከገለባው ለይቶ በሪቅ በጎታ በጎተራ የሚሰበስብበት ወኃሠሮስ ያውዒ በእሳት ዘኢይጠፍዕ። ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት የሚያቃጥል እሱ ያጠምቀክሙ በል ወደ ወርቅ ሂዶ ዘኢይጠፍዕ አለ ፤ እንድም ዘመሥኤ ብለህ መልስ ፡ ጣቱ ሦስት ነው ቢሉ የሦስትነት መያዣው ያንድነት ሁለት ነው ቢሉ ኄዑና ሐሩ የሚልበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን ።

ዘቦቱ ያነጽሕ ዓውደ እክሉ ዘውእቱ ፍጥረተ ሰብእ ብሎ ወሰዶታል ሊቁ ፡ ጻድቃንን ከኃጥአን የሚለይበት ።

ወያስተጋብእ ሥርናዮ ውስተ መዛግብቲሁ ፡ ጻድቃንን ከኃጥአን ለይቶ በመንግሥተ ሰማያት የሚያኖርበት ፡ መዛግብት ብሎ አበዛ በብዙ ወገን ትወረሳለችና ፡ እስመ ውስተ ቤተ አቡየ ብዙኅ ማኅደር ወምዕራፍ ቦቱ እንዲል ።

ወኃሠርሰ ያውዒ በእሳት ዘኢይጠፍዕ ፡ ኃጥአንን ከጻድቃን ለይቶ በገሃነም ሥቃይ የሚያመጣበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን ፡ እንድም ክፋውን ሕሊና ከበጎው ሕሊና የሚለይበት ሥልጣን ክህነት ገንዘቡ የሚሆን ፡ ወሥርናዮስ በጎውን ሕሊና ከክፉ ሕሊና ለይቶ በመንፈስ ቅዱስ የሚያስጠብቅበት እሱ ፤ መዛግብት ብሎ አበዛ ስለ ሀብቱ ብዛት ወኃሠርሰ ፤ ክፋውን ሕሊና ከበጎ ሕሊና ለይቶ በቀኖና የሚያጠፋበት ሥልጣን ክህነት ገንዘቡ የሚሆን እሱ በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያጠምቃችኋል

በእንተ ጥምቀተ እግዚእ
ኢየሱስ

፲፫ ወአሜሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ እምገሊላ ውስተ ዮርዳኖስ ከመ ይጠመቅ እምዮሐንስ

፲፫ ማር ፩ ፡ ፱ ። ለጌታ ሠላሳ ሲመላው ለዮሐንስ መንፈቅ ሲቀርበው ያን ጊዜ ጌታ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደዮርዳኖስ መጣ ። እንድም ሰው ሰብስቦ በሚያጠምቅበት ጊዜ መጣ እብ በደመና ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክር

መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመጥ አንድነት ሦስትነት ይታወቃልና ፣ ያን ጊዜ ጌታ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ አለ ። ሐተታ ምነው ባሪያ ወደ ጌታው ይሄዳል እንጅ ጌታ ወደ ባሪያ ይሄዳልን ፣ ባሪያ በጌታው እጅ ይጠመቃል እንጅ ጌታ በባሪያው እጅ ይጠመቃልን ቢሉ ጌታ መምጣቱ ለትሕትና ነው እንጅ ልልዕልና አይደለምና ፣ አንድም ለአብነትነት ጌታ ዮሐንስን መጥተህ አጥምቀኝ ብሎት ቢሆን ዛሬ ነገሥታት መኳንንት መጥታችሁ አጥምቁን ባሉ ነበርና ፣ ሂዳችሁ ተጠመቁ ለማለት አብነት ለመሆን ፣ ጥምቀቱን በዮርዳኖስ ያደረገው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ፣ ትንቢት ባሕርኒ ርእየት ወጎየት ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅሬሁ ርእዩከ ማያት እግዚኦ ርእዩከ ማያት ወፈርሁ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አንድ ነው ዝቅ ብሎ በደሴት ይከፈላል ከታች ወርዶ ይገናኛል ። ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አንድ እንደሆነ የሰው ሁሉ ነቁ አንድ አዳም ነው ። ዝቅ ብሎ በደሴት እንዲከፈል እስራኤል በግዝረት አሕዛብ በቍልፈት ተለያይተዋል ። ከታች ወርዶ በወደብ እንዲገናኝ ሕዝብና አሕዛብ በክርስቶስ በጥምቀት አንድ ሁነዋልና ፣ አንድም አብርሃም ላምስቱ ነገሥተ ሰዶም ረድቶ አራቱን ነገሥተ ኮሎዶጎምርን ድል ነሥቶ ቢመለስ ደስ ቢለው በመዋዕልየኑ ትፌኑ ቃለከ ወሚመ ታርእየኒ ኪያሃ ዕለተ አው አልቦ አለ ፣ እሱንስ እታየውም ምሳሌውን ታያለህና ሑር ዕድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ፣ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ አለው ፣ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ቢሄድ መልከ ጼዴቅ ኅብስተ በረከት ጽዋዓ አኰቴት ይዞ ተቀብሎታል አብርሃም የምእመናን ዮርዳኖስ የጥምቀት መልከ ጼዴቅ የቀሳውስት ኅብስተ በረከት ጽዋዓ አኰቴት የሥጋው የደሙ አንድም ኢዮብ ከዚህ ተጠምቆ ከደዌው ድኗል ፣ ኢዮብ የአዳም ከነሕፃናቱ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ፣ አንድም እሥራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል ፣ ምእመናንም አምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ገብተዋልና ፣ ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ገነት አርጓል ምእመናንም አምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ለመግባታቸው ። አንድም የኤልሳዕ ደቀ መዛሙርት ጸበበነ ማኅደር ንው ንግዝም ዕፀ ወንሕንጽ ካልዓ ማኅደረ ብለው ሄዱ ፣ እሱም መምህረ ትሕትና ነውና አብሯቸው ሄደ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ሲቆርጥ ምሳሩ ከዛቢያው ወልቆ ከባሕር ገባበት ፣ ዝኒ ኀዑይ እግዚአየ ፣ ጌታዬ ጥንቱን የተውሶ ያውም ጠፋ ተጨርሶ አለው የገባበትን አሳየኝ አለው አሳየው ቅርፍተ ዕፅ ቀርፎ አመሳቅሎ ቢመታው መዝቀጥ የማይቻለው ቅርፍተ ዕፅ ዘቅጦ መዝቀጥ የሚገባውን ብረት ይዞት ወጥቷል።እንደዚሁም ሁሉ ሞት የማይገባው መለኮት ሙቶ ሞት የሚገባው አዳምን ለማዳኑ ምሳሌ ፣ ጥምቀቱንም ሽቶ አላደረገውም ። አኮ ፈቂዶ ለተጠምቆ አላ ከመ የሀበነ ሱታፌ ንጽሕ እንዲል በመጠመቁም ጸጋ ያገኘበት አይደለም ። አኮ ዘረከበ ጸጋ በተጠምቆቱ አላ ከመ ያብርሀ መካናተ ወያኀይል ማያተ ለእለ ሀለዎሙ ይጠመቁ ውስቴታ እንዲል ፣ ዮርዳኖስን ብርሀት ማሕፀን ለማድረግ ለጥምቀት ኃይል ለመስጠት ነው እንጂ አንድም ዮርዳኖስ በበጋ የማይጎድል በክረምት የማይተርፍ ማእከላዊ ውኃ ነው የጌታም ጥምቀቱ እኛም ከመጥቀም በላይ እሱን ከመጥቀም በታች ነውና ፣ ዳግመኛ በባሕረ ጥብርያዶስ ላይ የሚሄድ ውኃ ነው ዐባይ በጣና ላይ እንዲሄድ የጌታም ጥምቀት ከኛ ጥምቀት በላይ ነውና ፤ አንድም ብዙ ንዑሳን አንቅዕት ይገቡበታል እሱ ያበረታቸዋል እንጂ እነሱ አያበረቱትም ፣ የጌታም ጥምቀት ለኛ ጥምቀት ኃይል ጽንዕ ይሆናል እንጂ የኛ ጥምቀት ለጌታ ጥምቀት ኃይል ጽንዕ አይሆንምና ። አንድም ንዕማን ከዚህ ተጠምቆ ከደዌው ተፈውሷል ንዕማን የአዳም ከነሕፃናቱ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ፣ ኢዮብን ዕማን ጌታ የተጠመቀበት ወደቡ አንድ ነው ። ትንቢቱን ዐውቆ አናግሯል ምሳሌውንም እንጂ ፀውቆ አስመስሏል ። ምሥጢሩ እንደምነው ቢሉ ዲያብሎስ የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ በአዳምና በሔዋን ሥቃይ አጸናባቸው ስመ ግብርናታችሁን ጽፋችሁ ብትሰጡኝ ባቀለልሁላችሁ ነበር አላቸው ። አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ ብለው ጽፈው ሰጡት መጽሐፍ የለም ይሁንብን ማለታቸውን መናገር ነው እንጂ እሱ በሁለት ዕብነ ሩካም ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ አንዱን በሲኦል ጥሎታል፣ በዮርዳኖስ የጣለውን ሲጠመቅ እንደ ሰውነቱ ተረገጠ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶላቸዋል ። በሲኦል የጣለውን በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ ነፍሳትን ሲያወጣ አጥፍቶላቸው ወጥቷል ።

፲፬ ወዮሐንስሰ ያበዮ እንዘ ይብል አንሰ እፈቅድ እምኀቤከ እጠመቅ ።

፲፬ ዮሐንስ ግን ባሪያ በጌታው እጅ ይጠመቃል እንጂ ጌታ በባሪያው እጅ ይጠመቃልን ብሎ አይሆንም አለው ።

ወአንተኑ ትመጽእ ኀቤየ ፤

ባሪያ ወደ ጌታው ይሄዳል እንጂ ጌታ ወደ ባሪያው ይሄዳልን አለው ፣ እናቱ ምንትኑ አነ ከመ ትምጽእ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ ብላ ነበርና ። ከዚያ አያይዞ እንዲህ አለ ።

፲፭ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ኅድግ ምዕረሰ ።

፲፭ ጌታ መለሰ አንድ ጊዜስ ተው አለው ። ሐተታ ፡ አንድ ጊዜ ቢጠመቅ ሁለተኛ ፡ በፈቃድ ቢጠመቅ በግድ ፡ በሰውነቱ ቢጠመቅ ባምላክነቱ መጠመቅ የለበትምና ።

እስመ ከመዝ ተድላ ውእቱ ለነ ይህ ለኛ ተድላችን ነውና ፤ ሐተታ ፡ ራሱን ከዮሐንስ አግብቶ አንተም መጥምቀ መለኮት ተብለህ ክብርህ ይነገራልና እኔም በባሪያው እጅ ተጠመቀ ተብሎ ትሕትናዬ ይነገራልና ወይደልወነ ከመ ንፈጽም ኵሎ ጽድቀ። ትንቢተ ነቢያትን ልንፈጽም ይገባናልና ዮሐንስ እንዲያጠምቅ ጌታ እንዲጠመቅ ትንቢት ተነግሯልና አንድም እስመ ከመዝ ተድላ ለነ ። ራሱን ከምእመናን አግብቶ ይህ ለኛ ተድላችን ነውና ፤ እናንተም ብትጠመቁ ይወርድላችኋል ለማለት ፡ ወይደልወነ ከመ ንፈጽም ኵሎ ጽድቀ ። ጽድቀ ተሰብአን ልንፈጽም ይገባናልና ፡ አንድም ራሱን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ አድርጎ ይህ ለኛ ተድላችን ነውና አለ ። አብ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመጥ አንድነት ሦስትነት ይገለጻልና ። ወይደልወነ ከመ ንፈጽም ኵሎ ጽድቀ ፡ በማኅፀን የጀመርነውን ቸርነት ልንፈጽም ይገባናልና ። ወእምዝ ኅደጎ ።

ከዚህ በኋላ ተወው ። ሐተታ ፡ እንዲያው አይተወውም ስመ አብ ብከ ወስመ ወልድ ለሊከ ወስመ መንፈስ ቅዱስ ሀለው ውስቴትከ ባዕደ አጠምቅ በስምከ ወበስመ መኑ አጠምቅ ኪያከ አለው ወልዱ ለቡሩክ ከማቴ ብርሃን ተማኅለነ ፡ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ብለህ አጥምቀኝ አለው ። ከዚህ በኋላ ተያይዘው ወደ ባሕር ወርደዋል ።

፲፮ ወተጠሚቆ እግዚእ ኢየሱስ ሶቤሃ ወፅአ እማይ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡

፲፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ከውኃው ወጣ ሐተታ ፡ ጥምቀቱን በውኃ ያደረገው በሌላ ያላደረገው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ፡ ትንቢት ወእነዝኃክሙ በማይ ንጹሕ ወትነጽሑ እምርኵስክሙ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም ለታውፅእ ባሕር ኵሎ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈስ ሕይወት ባለ ጊዜ በልብ የሚሳቡ በእግር የሚያሽከረክሩ በክንፍ የሚበሩ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ፍጥረታት ተገኝተዋል ፡ በረው በረው የሄዱ አሉ ከዚያውም የቀሩ አሉ ። በረው የሄዱ የኢጥሙቃን ከዚያው የቀሩ የጥሙቃን ምሳሌ ፡ ይህስ እንዳይሆን ወባረኮሙ ለክልኤሆሙ በአሐቲ በረከት ይላል ብሎ በልብ የሚሳቡ የሰብአ ዓለም በእግር የሚያሽከረክሩ ከትሩፋት ወደ ትሩፋት የሚሉ የባሕታውያን ፡ በክንፍ የሚበሩ ተመስጦ ያላቸው የሰማዕታት ምሳሌ ትንቢቱን ዐውቆ እናግሯል ፡ ምሳሌውንም እንጂ ባወቀ አስመሰሏል ፍጻሜው እንደምነው ቢሉ ውኃ በዙፋን ካለ ንጉሥ ባደባባይ እስካለ ጽኑስ ለሁሉ ርኩብ ነው ጥምቀት መሠራቱ ለሁሉ ነውና ፡ ውኃ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይፈሳል ። ጥምቀትም ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደረጋልና ። ውኃ ያነጻል ጥምቀትም ያነጻልና ፡ ውኃ ለወሰደው ፍለጋ የለውም በጥምቀትም የተሰረየ ኃጢአት በፍዳ አይመረመርምና ፡ ውኃ መልክ ያሳያል መልክ ያለመልማል ፡ ጥምቀትም መልክአ ነፍስ ያሳያልና መልክአ ነፍስ ያስመልማልና ፡ በውሀ የታጠበ ልብስ ኃይል ጽንዕ ግዘፍ እየነሣ ይሄዳል ምእመናንም ተጠምቀው ገድል ትሩፋት እያከሉ ይሄዳሉና ፡ አንድም ሥጋዊ ተፍኀሮ የነርብቃ የነሲፓራ በውኃ ምክንያት ሁኑዋል መንፈሳዊ ተፍኀሮንም በውኃ ለማድረግ ፡ አንድም ሸክላ ሠሪ ሠርታ ስትጨርስ የነቃባት እንደሆነ እንደገና ከስክሳ በውኃ ለውሳ ታድሰዋለች ። ተሐድሶም በጥምቀት ነውና ፡ አንድም በውኃ ቀድሞ ሰብአ ትካትን ኋላ ግብጻውያንን ካጠፋበት በኋላ ለመዓት እንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም ብለውታል ፡ ለምሕረትም እንደተፈጠረ ለማጠየቅ ። ሐተታ የወዲያኛው ቀስቱን እያጋለ መርዝ እየቀባ እያተባ ይመጣል ። የወዲህኛውም እግዚአብሔር ጥበቡን ገልጾለት ጀባውን ከውኃ ነከሮ ለጋሻው አልብሶ ይሄዳል መርዙን ጀባው ይጠርግለታል ፡ ግለቱን ውኃው ያቀዘቅዝለታል ስለቱን ጋሻው ይመልስለታል እንደዚህ ሁሉ ምእመናንም በጥምቀት ባገኙት ኃይል ድል ይነሣሉና ።

ወናሁ ተርኅወ ሎቱ ሰማይ ፡ ሰማይ ተከፈተለት ። ሐተታ ፡ በሰማይ መከፈት መዘጋት የለበትም ደጅ በተከፈተ ጊዜ የውስጡ እንዲታይ ያልተገለጸ ምስጢር ተገለጸለት ሲል ነው ። ወርእየ መንፈሰ እግዚአብሔር እንዘ ይወርድ ከመ ርግብ ወነበረ ላዕሌሁ። መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥበት አየ ። ሐተታ ፡ መንፈስ ቅዱስን ርግብ አለው ርግብ ኃዳጊተ በቀል ናት ። መንፈስ ቅዱስም ኃዳጌ በቀል ነውና አንድም ርግብ በኖኅ ጊዜ ሐጸ ማየ አይኅ ስትል ቆጽለ ዕፀ ዘይት ይዛ ተገኝታለች ፡ መንፈስ ቅዱስም ተስፋ መስቀልን ያበሥራልና ፤ አንድም ርግብ ከንፏን ቢመቷት ዕንቍላሏን ቢሰብሩባት ቤቷን ካፈረሱባት አትሄድም ። መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት ቢሠሩ ፈጽመው ካልካዱት አይለይምና ፤ ታሪክ ፡ አንድ ባሕታዊ እንዳየው ወለተ ካህን ግፎርን አጊጣ አይቶ

በሐጸ ዝሙት ተንደፈ ። ሳማባሽ አላት ላባቴ ንገረው እምቢ አይልህም አለችው ሂዶ ነገረው ። ፈጣሪዩን ልጠይቅ ብሎ ከጣዖቱ ዘንድ ገብቶ ልለጨው አልስጠው ብሎ ጠየቀው ። ቆቡን ይቅደድ ፈጣሪውን ይካድ ይኸን ካላደረገ አትስጠው አለው ሂዶ ነገረው። ቆቡን ቀደደ ፈጣሪውን ካደ ። በዚህ ጊዜ አድሮበት የነበረ መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ አምሳል ተለይቶት ሲሄድ አይቷል ። ያልኸኝን አደረግሁ ስጠኝ አለው ሁለተኛ ልጠይቅ ብሎ ገብቶ ቢጠይቀው ፤ ቆይ ፈጣሪውም ፈጽሞ አልራቀውም ባጠገብ ባጠገቡ ይጠብቀዋልና አትስጠው አለው ። አይሆንም አለው ፤ ለዚህን ብዬ ፈጣሪዬን ካድሁ ቆቤን ቀደድሁ ብሎ ንስሐ ቢገባ ተመልሶ በርግብ አምሳል ሲያድርበት አይቷል ። ጥምቀቱን በመዓልት ያላደረገው በሌሊት ያደረገው ስለምን ቢሉ ፤ በመዓልት አድርጎት ቢሆን መንፈስ ቅዱስን በቁሙ ርግብ ነው ብለው በተጠራጠሩ ነበርና አሁንስ በቁሙ ርግብ አለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ በምን ይታወቃል ቢሉ ፤ ጌታ የተጠመቀ ከሌሊቱ ባሥረኛው ሰዓት ነው በዚያን ጊዜ ተሐዋስያን ከየቦታቸው አይናወጡምና ፤ በቁሙ ርግብ አለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል፤ መንፈስ ቅዱስም መውረዱ ከውኃው ከወጣ ከዮሐንስ ዘተለየ ነው ። ከውኃው ሳለ ወርዶ ቢሆን ለቀድሶተ ማያት የወረደ ነው ባሉ ነበረና ከዮሐንስ ጋራም ሳለ ቢሆን ስለ ክብረ ዮሐንስ የወረደ ነው ባሉ ነበርና ፤ ረቦ ወርዷል ያሉ እንደ ሆነ አብ ምሉእ ነው አንተም ምሉእ ነህ እኔም ምሉእ ነኝ ሲል ፤ አሰይፎ ወርዷል ያሉ እንደሆነ የብሉይ መዋዕል የአብ ሕይወት ነኝ ብሉየ መዋዕል ያንተም ሕይወት ነኝ እኔም ብሉየ መዋዕል ሕይወት ነኝ ሲል ወርዶ ራሱን ቆንጠጥ አድርጎ ይዞታል አብ አኃዜ ዓለም ነው አንተም አኃዜ ዓለም ነህ እኔም አኃዜ ዓለም ነኝ ሲል ፤ መውረዱ ግን የማኅፀኑን ለመግለጽ ነው ። አንድም ለአብነት እናንተም ብትጠመቁ እንዲህ ይወርድላችኋል ለማለት ወናሁ መጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቀርኩ ዘቦቱ ሠመርኩ ። ሉቃ ፱ ፴፭ ፤ ፪ ጴጥ ፩ ፲፯።

፲፯ ለትዋሕዶ የመረጥሁት ብሎ ህልው ሆኜ ልመለክበት የወደድሁት ልጅ ይህ ነው የሚል ቃል ከወደ ሰማይ ተሰማ ሐተታ ፤ በዚሁ አድሮ ያለው ልጄ ነው አላሰም ፩ አካል ፩ ባሕርይ አድርጎ ይህ ልጄ ነው አለ እንጂ ፤ ኢይቤ ዘላዕለ ዝንቱ ወልድየ እላ ይቤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ እንዲል። ወልድየም ማለቱ እንደ አምላክነቱ ነው እንጂ እንደ ሰውነቱ አይደለም ። ኢይቤ ዝንቱ ወልድየ ዘከመ ትስብእቱ አላ ይቤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘከመ መለኮቱ እንዲል ።

ወእንተ ተመክሮት ዘኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወእምዝ ወሰዶ መንፈስ ገዳመ ለእግዚእ ኢየሱስ ። ማር ፩ ፤ ፲፪ ሉቃ ፬ ፩ ፤ ከተጠመቀ በኋላ ፈቃዱ አንሣስቶ ወደ ገዳም ወሰደው ። ወሶበ ትሰምዕ እንዘ ይብለከ መንፈስ ወሰዶ ገዳመ ኢትሐሊኬ ከመ ፍጡር ውእቱ ፤ አላ መንፈሰ ሥምረቱ ይእቲ እንዲል ፤ አንድም መንፈስ ቅዱስ የሚል አብነት ይገኛል ሰማዕታትን አንሣሥቶ ወደ ደም ጻድቃንን አንሣስቶ ወደ ገዳም እንዲወስድ ወሰደው ማለት አይደለም ፈቃዳቸው አንድ መሆኑን መናገር ነው ። ተጠምቆም አልዋለም አላደረም ዕለቱን ገዳም ሄዷል ። እናንተም ተጠምቃችሁ አትዋሉ አትደሩ ዕለቱን ገዳም ሂዱ ለማለት አብነት ለመሆን ወደ ገዳም ሄደ አለ ። አዳም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በገነት ድል ተነሥቶ ነበርና ፤ እሱም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በገዳም በጽኑ እርጅስተ ኃጣውእ ድል ለመንሳት ። አንድም በገዳም ጸር ይቀላል ለወጣንያን አብነት ለመሆን አንድም በገዳም ጸር ይጸናል ለፍጹማን አብነት ለመሆን ። ከመ ይትመከር እምዲያብሎስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ፤ እፈተናለሁስ ብሎ ሄዶ ቢሆን ዕዳ በሆነበት ነበር ፤ ከሄደ ዘንድ ጸሩን እየቀሰመ ይሰብርበታል እንጂ ።

ይሆንም ጸር እግርበታለሁ ብሎ አላደረገውም ንግሥ ፩ መዓዱ እምአፍአ ከመ ቀኩን ፍቱን ወሰብሎ እንዲል መከራውንም ሽቶ አላመጣውም እኮ ፈቃዶ መከራሁ ለጸላኢ አላ ከመ ያብጥል ኃይሎ ለዘያሚክር በኃይሉ ለቃል ዘኮነ ሰደ ምስለ ሥጋ እንዲል ። መከራውንም አንሣሥቶ አላመጣውም ኢሆከ እግዚእን እሎንቱ ሕማማቲ ከመ ይጎልፉ ዲቤሁ እላ በሁከቶሙ ማሰኑ እንዲል ፤ መዋጋቱም በሰውነቱ ነው ፤ ኢሠርዓ እግዚእን ቀትለ በመለኮቱ አላ በሥጋሁ ዘይትቄጸፍ ሕማማተ እንዲል ። ድል መንሳቱም በሰውነቱ ነው እንጂ በአምላክነቱ አይደለም። ወኢሞአ በኃይሉ መዋኢት እንዲል፤ በአምላክነቱስ ድል ቢነሳው ባልተደነቀም ነበር ፤ ሶበሰ ሞአ እግዚእን በኃይሉ መዋኢት እምኢኮነ መንከረ ወእም ኢኮኑ ትሩፋት ዘወሰከቶ ዘሌሰበ ሕቶወዘ ኢውድሰት እኮ መንከር እመ ምአ ኃይል ለድኩም እንዲል ።

፪ ወጾመ ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ

፪ ፵ መዓልት ፵ ሌሊት ጾመ ። ሠራዒ ሕግ ነውና ጾምን መጀመሪያ ሕግ አደረገ ። አንድም ሥራውን በጾም ጀመረ ። ሐተታ ፤ መብል ለኃጣውእ መሠረት እንደ ሆነ ፤ ጾምም ለምግባር ለትሩፋት መሠረት ናትና ፤ እማ ለጸሎት ወእኅታ ለእር

ምሞ ወነቅዓ ለአንብዕ ወጥንተ ኵሉ ገድል ሙናይት እንዲል ። ፵መዓልት ፵ ሌሊት መሆኑ ስለምን ቢሉ ቀድሞ አባቶቹ ነቢያት ፵ ፵ ጹመዋል ከዚያ ቢያተርፍ አተረፈ ቢያጐድል አጐደለ ብለው አይሁድ ደጊቱን ሕገ ወንጌልን ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና ፤ ሙሴ በ፵ ዘመኑ ለዕብራዊ ረድቶ ግብጻዊን ገድሎ በኖጻ ቀብሮታል ። ሙሴ የወልደ እግዚአ ዚአብሔር ዕብራዊ የአዳም ግብጻዊ የዲያብሎስ ኖጻ የመስቀል ። እንድም የ፫ቱ አርእስተ ኃጣውእ ምሳሌ ፤ ሙሴ ፵ ጹም ሕገ ኦሪትን ሠርቷል እሱም ፵ ጹሞ ሕገ ወንጌልን የሚሠራ ነውና ሙሴ ፵ ዘመን በምድያም ኑሮ እሥራኤልን ከግብጽ አውጥቷቸዋል ። እሱም ፵ ጹሞ

ነፍሳትን የሚያወጣ ነውና ፤ እንድም የእሥራኤል ጉበኞች በ፵ ቀን ተመልሰዋል ። እሱም የመንግሥተ ሰማይ ጉበኛ ነውና እሥራኤል በገዳም ፵ ዘመን ኑረው ምድረ ርስት ገብተዋል ። እናንተም ፵ ብትጾሙ ጊኒት መንግሥተ ሰማያት ትገባላችሁ ለማለት ። ኤልያስ ፵ ጹሞ ገነት ገብቷል ። እናንተም ፵ ብትጾሙ ገነት መንግሥተ ሰማያት ትገባላችሁ ለማለት ሕዝቅኤል በፀጋማይ ጐኑ ፵ ቀን ተኝቶ ሰድስት መቶ ሙታን አስነሥቷል ። እናንተም ፵ብትጾሙ ትንሣኤ ዘለክብር ትነሣላችሁ ለማለት ፤ ዕዝራ ፵ ቀን ከምግቡ ተከልክሎ መጻሕፍትን አጽፏል ። እንሰ በውእቶን መዋዕል ኢበላዕኩ እክለ ወኢሰተይኩ ማየ ። እመንቱስ መዓልተ ይጽሕፉ ወሠርከ ይዴረሩ እንዲል እነዚያ ቀን ሲጽፉ እየዋሉ ማታ ይመገባሉ ። እሱ ግን ቀን ሲያጽፈው የሚውለውን ሌሊት ሲያስበው ያድር ነበር ። እናንተም ፵ ብትጾሙ ምሥጢር ይገለጥላችኋል ለማለት ፤ እባብ አካሉ የደገደገበት እንደሆነ ፵ ቀን ከምግብ ተከልክሎ ይሰነብታል ። በስቁረተ ዕፅ በስቁረተ እብንም ቢሉ አልፎ ሲሄድ ተግፎ ይወድቅበታል ይታደሳል ። እናንተም አርባ ብትጾሙ ተሐድሶተ ነፍስ ታገኛላችሁ ለማለት ። ምሳሌውን አውቆ አስመስሏል ፍጻሜው እንደም ነው ቢሉ አዳም በ፵ ቀን ያገኘውን ልጅነት አስወስዶ ነበርና ለሱ እንደካስ ለማጠየቅ ፤ እንድም በ፵ቀን ተሰእሎተ መልክእ ለተፈጸመለት ሰው ሁሉ ሊክስ እንደመጣ ለማጠየቅ ። ፵ቱ ባሕርያት ፀሥር ዐሥሩን ለመካስ ። አምስተኛ ባሕርዩ ነፍስን የጨመሩ እንደሆነ ስምንት ስምንቱን ሊክስ እንደመጣ ለማጠየቅ ። ከዚህም ተራብ አልሳሳም ተዋጋ ድል አልተነሣም ወሶበ ጾመ እግዚእ ፵መዓልተ ወ፵ሌሊተ ከሠተ ከመ ኢሐመ ሥጋሁ እምረኃብ ወጽምዕ በኃይል ዘይደሉ ለመለኮት እንዲል ፤ ከዚህም ሥራውን ሠርቶ ሥሩ አለ እንጂ ። ባልዋጄበት ጣት የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበት እንዲሉ ሳይሠራ እኛን ሥሩ አላለንም ወሐርን እግዚእ ለጼስ ግብራት እንዲል ፭ ግብራት የተባሉ ጥምቀት ፤ ተአምኖ ኃጣውእ ከዊነ ሰማዕት ተባሕትዎ ምንኵስና ። ጥምቀት በእደ ዮሐንስ መጠመቅ ተአምኖ ኃጣውእ ከተአማንያን ኃጣውእ ጋራ አንድ ሁኖ መቆጠር ከዊነ ሰማዕት አንሰ በእንተ ዝንቱ ተወለድኩ ወእንበይነ ዝንቱ መጻእኩ ውስተ ዓለም ከመ እኩን ሰማዕተ በጽድቅ ብሎ ከጲላጦስ ፊት ቁሞ መመስከር ተባሕትዎ ፵ ቀን ከምግብ ተከልክሎ በገዳም መኖር ፤ ምንኵስና በድንግልና መኖር ነው ። ረቂቅ ዘእምረቂቅ እንደሆነ ለማጠየቅ በጎቱም ድንግልና ተፀነሰ በጎቱም ድንግልና ተወለደ ። ዘኢይርኅብ እምዘኢይርኅብ እንደሆነ ለማጠየቅ ፵ መዓልት ፵ሌሊት ጾመ ዘኢይትገሠሥ እምዘኢይትገሠሥ እንደሆነ ለማጠየቅ በባሕር ላይ ሄደ ። ብርሃን ዘእምብርሃን እንደሆነ ለማጠየቅ ብርሃን መለኮቱን በደብረ ታቦር ገለጸ ሕይወት ዘእምሕይወት እንደሆነ ለማጠየቅ ያራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን አነሣ ። ወእምዝ ርኅበ ፤ ከዚህ በኋላ ተራበ ። ሐተታ ረኃቡም የፈቃድ ረኃብ ነው እጂ እንደኛ ረኃብ አይደለም እኛ ብንበላው ቁንጣን ብንተወው ስልት ቀጠና ይሆንብናል ፤ ረኀበ እግዚአነስ እኮ ከመ ረኃበ ዚአነ እላ ገጸ ረኃቡ ፍሉጥ እምኔነ ሰነስ በግብር ይመውእነ ወሎቱስ በፈቃዱ እንዲል ፤ አንድ ጊዜ ርኅበ አንድ ጊዜ ኢርኀበ ይላል እንደምነው ቢሉ ፤ ከ፪ቱ አካል ፩ አካል ከሁለት ባሕርይ ፩ባሕርይ እንደሆነ ለማጠየቅ ። በእንተ ምንት ርኅበ እግዚእነ ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ ያጠይቅ ከመ ውእቱ እም ፬ ሀባዌያት እንዲል ። መራቡም ለአጽድቆተ ትስብእት ለካሣ ነው ።

፫ ወቀርበ ዘያሜክር ።

፫ የሚፈታተነው ዲያብሎስ ቀረበ ሐተታ እንዲያው አይቀርበውም ርኅብኩ የሚል ድምፅ ሰምቶት ፍሬ ዕፅ ሲሻ አይቶት ፤ መልኩን አጠውልጎ ታይቶት እሱም እንዲያው አይቀርብም በአምሳለ ሠዓሊ በአምሳለ ሐራሲ በቀዳዳ ሽልቻ ትኩስ ዳቦ የያዘ መስሎ ሁለት ደንጊያ ይዞ ይቀርባል አንዱን ላተ አንዱን ለኔ ዳቦ አድርገህ እንብላ እለዋለሁ ደንጊያውንማ ዳቦ ከማድረግ የያዝኸውን እንበላም ያለኝ እንደሆነ አዳምን አባቱን በመብል ምክንያት ድል እንደነሣሁት እሱንም በመብል ምክንያት ድል እነሣዋለሁ ብሎ ፤

ወይቤሎ እመሰ ወልደ እግዚአብሔር አንተ በል ከመ እላ ኢዕባን ኅብስተ ይኩና ፤

በዮርዳኖስ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክርለት ሰምቶ ነበርና የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እኒህ ደንጊያዎች ኅብስት ይሁኑ ዘንድ እዘዝ አለው ። ቢያደርገው የሰይጣን ተአዛዚ ብየ ዕዳ እልበቃለሁ

ባያደርገው ደካማ እሰኘዋለሁ ። ቢያደርገው ሌላ ጾር እሻለታለሁ ባያደርገው ድካሙን አይቼ እቀርቧለሁ ብሎ ፤ ድንጊያውን ኅብስት አድርግ ማለቱ ምን ልማድ ይዞ ነው ቢሉ በዮሴፍ ልማድ ፤ ዮሴፍን እባቱ የሱን ስንቅ ሉብቻ አሲዞ ለወንድሞችህ ስንቃቸውን ሰጥተህ ወንድሞችህን ጠይቀህ ና ብሎ ላከው ። ያሉበትን እጥቶ ሲፈልግ የሱ ስንቅ አለቀበት ከዚያ እንዳይጠፋ አባቱ ያላዘዘው ነው ። ረኃብ ጸንቶበት ሳለ መልአክ ያጣትህን ፈጣሪ ድንጊያውን ዳቦ አድርግልኝ አትለውም አለው ። ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ድንጊያው ዳቦ ሁኖለት ተመግቧልና እንዲህ አለ ።

፬ ወእውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ጌታም መለሰ ። ወይቤሎ ጽሑፍ ከመ አኮ በኅብስት ከመ ዘየሐዩ ሰብእ ። ዘዳ ፰ ፫ ሉቃ ፬፥፬ ።

፬ ሰው የሚድነው በኅብስት ብቻ እንዳይደለ ተጽፏል ።

አላ በኵሉ ቃል ዘይወፅእ እምአፉሁ ለእግዚአብሔር እግዚአብሔር ዳን ያለው ይድናል ሙት ያለው ይሞታል እንጂ ፤ አንድም ሰው የሚያድን ገበሬ በጻረበት በኅብስት ብቻ እንዳይደለ ተጽፏል ፤ እግዚአብሔር ምግብ ይሁን ያለውም ምግብ ይሆናል እንጂ እስራኤል ፵ ዘመን በትርሀ አልወደቀ ጫማህ አልወለቀ ልብስህ አላለቀ እንዲሉ ከውቅያኖስ በደመና አይበት ተቋጥሮ በነፋስ ወደልጋዝ ተጭኖ መጠኑ ድንብላል እህሉ መልኩ በረድ መስሎ ወእንዘ የኃድግህቦ ይላል የውርጭ ገበታ ሲነጸፍ እየዘነመላቸው አርባ ዘመን ተመግበዋልና ፤ አንድም ሰው የሚድን ገበሬ በጻረበት ቢጋረበት በእንጀራ ብቻ እንዳይደለ ተጽፏል ፤ በዓቂበ ሕግም በትምህርትም ነው እንጂ ሐተታ ። የሰው ባሕርዩ ባሕርይ እንስሳዊ ባሕርይ መልአካዊ ነው ባሕርይ እንስሳዊ ምግብ ሲያጣ ይጎዳል ፤ ባሕርይ መልአካዊ ትምህርት ሲያጣ ይጎዳልና እእምር ከመ በእማን ቢያይ ቃለ እግዚአብሔር ሲቤተ ልብ ቃላቲሁ ለእግዚአብሔር ወእምጽእ ረኃበ እክል ወጽምዓ ማይ ለብሔር ረኃብስ እምስሚዓ ቃለ እግዚአብሔር እንዲል ። እንድም ወልደ እግዚአብሔርስ ከሆንህ ይህ እንደ ድንጊያ ፈዞ ያለ ሰውነትህ ኅብስተ ሕይወት ኅብስተ መድኃኒት ይሁን ብለህ እዘዝ ሲያሰኘው ነው ። ጌታም ሰው የሚያድን በዕሩቅ ብእሲ ሥጋ እንዳይደለ ተጽፏል ። አካላዊ ቃል በተዋሐደው ሥጋ ነው እንጂ አለው ፭ ወእምዝ ነሥኦ ወወሰዶ ውስተ ቅድስት ሀገር ።

፭ ከዚህ በኋላ ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ወሰደው ሐተታ እሱስ አይወስደውም ፈቃዱን ዐውቆ ስለሄደለት ካህናትን ድል ነሥቼበት በማላውቅ በገዳም ቢሆን ነው እንጂ ፤ ካህናትን ድል በምነሳበት በቤተ መቅደስ ቢሆን መች ድል ይነሳኝ ነበር ብሏል ፈቃዱን አይቶ ስለሄደለት ነሥኦ ወሰዶ አዕረጎ ይላል ወዓቀሞ ውስተ ተድባበ ቤተ መቅደስ ። ተድባብ ማዕዘንት ርእስ ይላል አብነት ፤ ተድባብ ያለ እንደሆነ ከዝንቦው ማዕዘንት ያለ እንደሆነ ከምሕዋሩ ርእስ ያለ እንደሆነ ከጉልላቱ አቆመው ። ከዚህም በአምሳለ ሊቀ ካህናት እምሞ ጠምጥሞ መነሳንስ ይዞ ይታየዋል ።

፮ ወይቤሎ እመሰ አማን ወልደ እግዚአብሔር አንተ ቅንጽ እምዝየ ወተወረው ታሕተ ።

፮ መዝ ፤ ፲፩ ።
በእውነት ወልደ እግዚአብሔር ከሆንህ ከዚህ ዘለህ ወደታች ውረድ አለው ፤ ሐተታ ቢሰበር ዐርፈዋለሁ ባይሰበር ምትሐት እሰኘዋለሁ ቢያደርገው ሌላ ጾር እሻለታለሁ ባያደርገው ደካማ እሰኘዋለሁ ቢያደርገው የሰይጣን ተእዛዚ ብየ ዕዳ እልበታለሁ ባያደርገው ድካሙን አይቼ እቀርበዋለሁ ብሎ ነው ። እስመ ጽሑፍ ከመ ለመላእክቲሁ ይኤዝዞሙ በእንቲአከ ከመ ይዕቀቡከ በኵሉ ፍናዊከ በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክትን ሰላንተ እንዲያዛቸው ተጽፏልና ፤ ወበእደዊሆሙ ያነሥኡከ ከመ ኢትትዐቀፍ በእብን እግርከ እግረከ ይላል ፤ እግርህ እንዳይሰናከል፤በእጆቻቸውም ያነሡሃል የሚል ጽሑፍ አለና ፤ ጌታ ከላይ ጠቅሶበት ነበርና ፤ እሱም ፈንታውን ይንጐዳጐዳል ።

፯ ወእውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ካዕበ ጽሑፍ ኢታመክሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ።
፯ ፤ ዘዳ ፡ ፲ ፤ ፲፮ ።

ዳግመኛ ፈጣሪህን እግዚአብሔርን አትፈታተነው የሚል ጽሑፍ አለ አለው ፤ እንዲህ የሚል ከምን አለ ቢሉ እንደ ጊዜ ገድሉ ጠቀሰ ። እሥራኤል በገዳም ሳሉ ሙሴ ካሥራሁለቱ ነገድ አውጥቶ ኢያሱና ካሌብን ምድረ ርስትን ሰልላችሁኑ ብሎ ሰደዳቸው ። እሶቸውም ሰልለው ሲመለሱ ከወይኑ ዘለላ ከስንዴው ዛላ በባጢ ቀፎ ይዘው መጡ ። እንደምን ሁናችሁ መጣችሁ ሀገሪቱስ እንደምን ያለች ናት ብለው ጠየቋቸው ። ሀገሪቱስ መልካም ናት እንደዚህ ያለ ታፈራለች ፤ ባሕቱ ርኢነ ደቂቀ ለኤናቅንኖሙ ከመ አርዝ ወጽንዖሙ ከመ አውልዐ ንሕነሰ ኮነ ከመ አናብጥ በቅድሜሆሙ ምድርኒ ትረድእሙ ወተዓቅቦሙ ብለው ፲ሩ አስገርመው አስፈርተው ተናገሩ ካሌብና ኢያሱ በፈቃደ እግዚአብሔር እንገባታለን አሉ ፲ሩ ካገባንስ አሁን ያገባን ሙሴ ተነሣ ታቦተ ጽዮንንም አንሣ እንሂድ አሉት ፤ ሙሴ ታቦተ ጽዮንም አሁን አትነሣ እናንተም እግዚአብሔር ፈጣሪያችሁን አትፈታተኑት አላቸው ። አይሆንም ብለው ሄዱ ። በወሰን ያሉ አሕዛብ ገጥመው

ድል አደረጋቸው ፤ በዚህ ጊዜ ከባሕር ጠልቀው ። ከገደል ወድቀው አልቀዋል ፤

ከዚህም ጌታ እንደ ጊዜ ገድሉ ጠቀሰው ።

፰ ወእምዝ ነሥኦ ዲያብሎስ ወአዕረጎ ውስተ ደብር ነዋኅ ጥቀ

፰ ከዚህ በኋላ ወደ ረጅም ተራራ አወጣው ሐተታ ነገሥታትን ድል በማልነሣበት በቤተ መቅደስ ቢሆን ድል ነሣኝ እንጂ ፣ ነገሥታት ድል በምነሣበት በተራራ ቢሆን መቼ ድል ይነሣኝ ነበር ብሏል ፈቃዱን ዐውቆ ስለሄደለት አዕረጎ አለ ።

ወአርአዮ መንግሥታተ ኵሉ ዓለም ፣ ወኵሎ ክብሮ ፣ ጠጠሩን ወርቅ ብር ፣ ቅጠሉን ግምጃ አስመስሎ አሳየው እንድም መንግሥታተ ኵሉ ዓለም ። ግዛቱን ሁሉ አሳየው ወኵሎ ክብሮ እንስሳትን አራዊትን ፈረስ በቅሎ ሠራዊት አስመስሎ አሳየው ፣ እሱስ ያይለታል ቢሉ ስለመሰለው ነው እንጂ አያይለትም ድል መንሳቱ በምን ይታወቃል ቢሉ ባለመጽነኑ ።

፱ ወይቤሎ ዘንተ ኵሎ እሁበከ እምከመ ሰገድከ ሊተ ወአምኀከኒ ፣ ደፋር ነውና ብትሰግድልኝ እጅ ብትነሳኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው ።

፲ ወእምዝ ይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን ።

፲ ዘዳግም ፮ ፲፫ ፣ ከዚህ በኋላ ከኋላየ ወግድ አለው ራስ አይቶ የሚመጣ ጠላት ክፉ ነውና ጽኑ ባላጋራዬ ሲል ነው ። ወዓቀመ አዴርሃ ሰይጣነ ላዕለ ሰሎሞን እንዲል ። እንድም እምዘድኅሬየ ይላል አብነት ከኔ በኋላ ከሚነሱ ከምእመናን ወግድላቸው አለው ። እንዲህ ባለው ጊዜ እንደጢስ ተኖ እንደ ትቢያ በኖ ጠፍቷአል ። ሐተታ እስካሁን ሑር አላለው አሁን ሑር ማለቱ ስለምን ቢሉ ። በቀዳሚ ጊዜ ጉየይ ወበካልዕ ጊዜ ጉየይ ወበሣልስ ተንሥአ ወተቃተል እንዲል ፣ አብነት ለመሆን በሦስተኛው ድል ንሱ ለማለት ንጉሥ በመንግሥቱ ጉልማሳ በሚስቱ እንዲቀና ፣ ጌታም ስአምልኮቱ ቀናዒ ነውና ፣ እስመ አነ አምላክ ቀናዒ ዘእፈዲ ኃጢአተ አብ ላዕለ ውሉድ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ለእለ ይጸልዑኒ ። ወለእለሰ ያፈቅሩኒ እገብር ምሕረተ እስከ ፲ቱ፻ ትውልድ እንዲል ።

ጽሑፍ ለእግዚአብሔር አምላክከ ትሰግድ ወኪያሁ ባሕቲቶ ታምልክ ፣ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ትሰግድ ዘንድ እሱንም ብቻ ታመልክ ዘንድ ተጽፏል አለው። ሑር እምድኅሬየ ባለው ጊዜ እንደጢስ ተኖ እንደ ትቢያ በኖ ጠፋ አላለምን ለማን ይጠቅስዋል ቢሉ ሰይጣንና ውሻ ምልልስ ወዳጅ ነውና ተመልሶ ያሰማዋል ። እንድም እንደ አምላክነቱ አጽንቶት ሰምቶ ይሄዳል ። እንድም ወጺጋሁ ታሰምዖ እንዲል ካለበት ሁኖ እንዲሰማው አድርጎታል ። እንድም ክሕተታ ለመዳን ጥቅሱ ይቀድማል ።

፲፩ ወእምዝ ኀደጎ ዲያብሎስ ።

፲፩ ከዚህ በኋላ ተወው እስከ ጊዜሁ ብሎ በሉቃስ ያቀናዋል ። በዕለተ ዓርብ በአይሁድ ሥጋው ሁኖ እስኪያስቅለው ድረስ አይመለስበትም ። ከዚህም በኃ ልጅ ተወልዶ ለአዳምና ለሔዋን በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ነሣላቸው ። አሁን ዛሬ ደም ያለበት ሰው ጌሻ አስነሥቶ አምባውን ሰብሮ ደመኛውን ገድሎ ደሙን መልሶ ቢሄድ የቀሩት ከዛፍ ከገደል ተጣግተው የሆነስ ሆነ አንተ ማነህ እንወቅህ ባሉት ጊዜ የዘመዶቼን የእገሌ የእገሌ ደም የማይቀርብኝ እኔ እገሌ ነኝ ብሎ እንዲል ፣ ጌታም የአባቴ የአዳም የእናቴ የሔዋን ደም የማይቀርብኝ ሲል በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ነሣላቸው ፣ ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ስስዕ ትዕቢት ፍቅረ ንዋይ ናቸው ። ስስት ያልሰጡትን መሻት ነው ። ትዕቢት አምላክ እሆናለሁ ማለት ነው ። ፍቅረ ንዋይ በቃኝ አለማለት ነው ። በዚህ ሁሉ ድል ነሥቶታል ። ዛቲ ሰፍጠት አንተ ረሰየቶ ለአዳም ይትመየጥ ውስተ መሬት ወሶበ በጽሐ ኀበ አምላኪየ ወኀቤ ሲሳይ ለኵሉ ገብአ ሰይጣን ተኃሬሮ ወተመዊኦ

እንዲል ፡ እንድም ድል መንሳቱ ለአዳምና ለሔዋን ብቻ አይደለም ለሁሉም ድል ነሥቶላቸዋል የመነኰሳትም ጾራቸው ስስት ነው በሹት ጊዜ አያገኙትምና በትኅርምት ኑዋሪዎች ናቸው በቦታቸው በገዳም በስስት ቢመጣበት በትዕግሥት ድል ነሥቶላቸዋል የካህናት ጾራቸው ትዕቢት ነው እእምሯችን ረቂቅ ማዕርጋችን ምጡቅ እያሉ ይታበያሉ ፣ በቦታቸውም በቤተ መቅደስ በትዕቢት ቢመጣበት በትሕትና ድል ነሥቶላቸዋል ። የነገሥታት ጾራቸው ፍቅረ ንዋይ ነው ቤታቸውን ከፍ ካለ ቦታ ሠርተው ያለፈ ያገደመውን የወጣ የወረደውን እያዩ የዚህ ሁሉ እንጅ ኑሮው በኛ ነው እያሉ ገንዘብ ይሰበስባሉ ቦታቸው በተራራ ነው ። በተራራ በፍቅረ ንዋይ ቢመጣበት በጸሊዓ ንዋይ ድል ነሥቶላቸዋል ፣ ከዚህ በኋላ ኃጢአት ከሥሩ እንደተነቀለ ዛፍ ሁናለች ከሥሩ የተነቀለ ዛፍ እንዳይለመልም እንዳያብብ እንዳያፈራ ኃጢአትም በፍዳ የማታሲዝ ሆናለች ። ዛሬ የተያዙ እሉሳ ቢሉ አሊህማ ዐዋጅ አፍራሾች ናቸው ። ንጉሥ ይዘምታል ድል ነሥቶ ሲመለስ ከመንገድ የወጣህ ወታደር ብሎ ዐዋጅ ይነግራል በደለኛ ወታደር ገንዘብ ሲዘርፍ ከመንደር ገብቶ ቢሞት ንጉሥ ድል አልነሣም ይባላልን ? እኒህስ ዐዋጅ አፍራሾች ናቸው ።

ወናሁ መጽኡ መላእክት ይትለአከዎ ።

አርባ ቀን በትህርምት ኖሯልና መላእክት ኀብስት ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ ይዘው መጡ እንድም ድል

ነሥቷልና ለከ ኃይል ለከ ጽንዕ እያሉ እያመሰገኑ ቀረቡ ። እንደ ዓቢይ ንጉሥ እንደ ንዑስ ንጉሥ ተሰልፈው ስንብተዋል ። ከዚህ በኋላ ሠራዊታችን ለምን ያልቃል አንድ ላንድ እንገናኝ ብለው ተገናኙ ። ዓቢይ ንጉሥ ንዑስ ንጉሥን ገደለው ። የዓቢይ ንጉሥ ሠራዊት ደስ ብሏቸው እየዘፈኑ ቀርበዋል ። የንዑስ ንጉሥ ሠራዊት እያዘኑ እየፈሩ ሸሽተዋል ። እኒህም ድል ነሥቶላቸዋልና ፥ መጡ አለ ። ድል ከነሣ በኋላ መምጣታቸውስ ስለምን ቢሉ አስቀድመው መጥተው ቢሆን መላእክትን ይዞ ድልነሣኝ እንጂ ብቻውንማ ቢሆን መች ድል ይነሣኝ ነበር ባለ ነበርና እንዲህ እንዳይል ። አንድም እናንተም ድል ብትነሱ ይገለጽላችኋል ለማለት ። አንዳንድ ባሕታዊ ሰይጣን መጥቶ ንጉሥ ይጠራሃል አለው ። አልብየ ንጉሥ ዘእንበለ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አለው ፤ ይህ ደፋር በዓለም እያለ ንጉሥ የለም ይላል ብሎ በያዘው በሎታ ተቀጥቅጦት ሄደ ። ከዚህ በኋላ መልአከ ዑቃቢው ተገለጸለት ማነህ አለው እኔ መልአከ ዑቃቢህ ነኝ አለው ። እንኪያ እስካሁን ወዴት ኖረሃል አለው አሁንም ድል ብትነሣ ነው እንጂ ድል ባትነሳ አልገለጽልህም ነበር ብሎታል ።

ዘከመ ነበረ እግዚእ ኢየሱስ በቅፍርናሆም ።

፲፪ ወሰሚዖ እግዚእየ ኢየሱስ ከመ አኀዝዎ ለዮሐንስ ተግኅሠ ውስተ ገሊላ ። ማር ፩፥፲፬ ።

፲፪ ከመ አኃዝዎ ከመ ተግኅሠ ይላል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐንስን እንዳጋዙት ዮሐንስ እንደተጋዘ በሰማ ጊዜ ገሊላ ገባ መከራ በመጣባችሁ ጊዜ ሽሹ ለማለት አብነት ለመሆን ።

፲፫ ወኃደጋ ለናዝሬት ወመጺአ ኀደረ ቅፍርናሆም እንተ መንገለ ባሕር ።

፲፫ ናዝሬትን ትቶ በባሕር አጠገብ ባለች በቅፍርናሆም ሲያስተምር ኖረ ። ውስተ አድባረ ዛብሎን ወንፍታሌም ። የዛብሎን የንፍታሌም ዕፃ በምትሆን

፲፬ ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ በኢሳይያስ ነቢይ

፲፬ በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል የተነገረው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ኖረ ።

፲፭ እንዘ ይብል ምድረ ዛብሎን ወምድረ ንፍታሌም ። ኢሳ ፱፥፩ ።

፲፭ በዛብሎን በንፍታሌም ዕፃ ያሉ ፍኖተ ባሕር ። በባሕር አጠገብ ያሉ ጺራልዩ ወጺራልያስ ። ጠጠር ገጠር ።

ማዕዶተ ሐይቀ ዮርዳኖስ ። በዮርዳኖስ ወደብ ማዶ በአንጻረ ሊባኖስ ያሉ ፥ ገሊላ ዘአሕዛብ የአሕዛብ ክፍል ዕፃ በምትሆን በገሊላ ያሉ ሐተታ ዘሕዝብ አለና ከዚያ ሲለይ ዘአሕዛብ አለ ፤ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን በሠራ ጊዜ ወአርድአ ኪራም በዕፀወ ቄድሮስ ወጺውቄና እንዲል ፤ ጥድ ዘግባ እየጠረበ አግዞታል ሃያ ያህል ቀላል ቀላል አህጉር ሰጠው እስመ ኢዓደማሁ ይላል ደስ ባያሰኙት ወዳጄ በኔና ባንተ ዘንድ ይህ ምን ቁም ነገር ነው አለው ። የመልክተኛ ማደሪያ ይሁንህ ብዩ ነው አለው ከዚህ በኋላ አሕዛብ እንደ ባለጉልት እሥራኤል እንደ ባለርስት ሁነው የሚኖሩ ሁነዋልና ገሊላ ዘአሕዛብ አለ ፤ አንድም ፈርዖን አሕዛብን ወግቶ ለልጁ ለሰሎሞን ሚስት ሰጥቷት ነበርና ገሊላ ዘአሕዛብ አለ ።

፲፮ ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእየ ብርሃነ ዓቢየ ፤

፲፮ በጨለማ ያሉ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን ወጣላቸው ። ወለእለሂ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ብርሃን ሠረቀ ሎሙ በጨለማ በሞት ጥላ ለሚኖሩ ብርሃን ወጣላቸው ብሎ ኢሳይያስ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ በቅፍርናሆም ኖረ ። አንድም በድንቁርና በቀቢጸ ተስፋ ለነበሩ ሰዎች ዕውቀት ተሰጣቸው ፤ አንድ ገጽ በማለት ሞትን በመምሰል ሞት ባመጣው ምስል ለሚኖሩ ሰዎች ክርስቶስ ተወለደላቸው ወንጌል ተጻፈላቸው ።

አንድም በሞተ ሥጋ በሞተ ነፍስ ለነበሩ ልጅነት ተሰጣቸው ። በኃጢአት በክህደት ለነበሩ ሃይማኖት ተገለጸላቸው ። ሐተታ ኃጢአትን ጽልመት ክህደትን ጽላሎተ ሞት አለው በጨለማ ላይ የዛፍ የገደል ጥላ የተጨመረ እንደሆን ጨለማው እንዲጠና በኃጢአትም ላይ ክህደት የተጨመረ እንደሆነ ፍዳው ይጸናልና ፤

፲፯ ወእምአሚሃ አኀዘ እግዚእ ኢየሱስ ይሰብክ ወይብል ነስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ። ማር ፩፥፲፭ ።

፲፯ ዮሐንስ ከተጋዘበት ቀን ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደጊቱ በልጅነት ልጅነት በሃይማኖት ልትሰጥ ቀርባለችና እመኑ እያለ ያስተምር ጀመረ ዮሐንስ ከተጋዘ በኋላ ማስተማሩ ስለምን ቢሉ መምር ሳለ በመምር ላይ እናስተምራለን አትበሉ ለማለት ። አንድም መምሩ አንድ ዮሐንስ ነበረ ያውም ተመተረ እንዳይሉ ትምህርቱንም አለወጠውም የሰንቱን ይስሟል እንዳይሉ ፤ አንድም ዮሐንስ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ብሎ ያስተማረልኝ እኔ ነኝ ሲል ነው ፤ ነያ ይሰምያ መንግሥተ ሰማያት ለአስተርእዮቱ ማእከለ ፍቁራኒሁ እንዲል ።

በእንተ ቀዳማውያን ሐዋርያት

፲፰ ወእንዘ ያንሶሱ መንገለ ባሕረ ገሊላ ርእየ ፪ተ አኃው ። ማር ፩፥፲፮ ።

፲፰ በገሊላ ባሕር ማዶ ሲመላለስ ሁለት ወንድማማቾች አገኘ ። ስምኦንሃ ፤ ዘተሰምየ ጴጥሮስ ። ጴጥሮስ የተባለ ስምኦንን ። ወእንድርያስሃ እኅዊሁ

ወንድሙን እንድርያስን እንዘ ይወድዩ መርበብቶሙ ውስተ ባሕር ፤ መረባቸውን ከባሕር ሲጥሉ እስመ መሠግራን እሙንቱ ዓሣ ወጋሮች ነበሩና ።

፲፱ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ንዑ ትልዉኒ ድኅሬየ ።

፲፱ ለጊዜው በእግር ተከተሉኝ ፍጻሜው በግብር ምሰሉኝ አላቸው ወእሬስየክሙ መሠግራነ ሰብእ ሰውን እንደ ዓሣ ወንጌልን እንደ መረብ ይህን ዓለም እንደ ባሕር አድርጋችሁ እንድታስቀምሩ አደርጋችኋለሁ አላቸው ።

፳ ወበጊዜሃ ኀደጉ መሠግሪሆሙ ወተለውዎ

፳ ያን ጊዜ ፈጥነው መርከባቸውን መረባቸውን ትተው ተከተሉት ለጊዜው በእግር ተከተሉት ፍጻሜው በግብር መሰሉት ።

፳፩ ወተዓዲዎ ሕቀ እምህየ ርእየ ካልዓነ ፪ተ አኃወ ።

፳፩ ከዚያ ጥቂት እልፍ ብሎ ሁለት ወንድማማች አገኘ ፤ ያዕቆብሃ ወልደ ዘብዴዎስ ወዮሐንስሃ እኅዋሁ ፤ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብን ወንድሙ ዮሐንስን ፤ ውስተ ሐመር ምስለ ዘብዴዎስ አቡሆሙ ፤ ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋራ እንዘ ይሠርዑ ወያስተሣንዩ መሣግሪሆሙ ።

መረባቸውን ያደፈውን ሲያጥቡ የተቀረጠውን ሲቀጥሉ ፣ ወጸውዖሙ ። ለጊዜው በእግር ተከተሉኝ ፍጻሜው በግብር ምሰሉኝ አላቸው ።

፳፪ ወበጊዜሃ ኀደጉ ሐመሮሙ ወዘብዴዎስሃ አባሆሙ ወተለውዎ ።

፳፪ ያን ጊዜ ፈጥነው መረባቸውን መርከባቸውን ዘብዴዎስ አባታቸውን ትተው ተከተሉት ፤ ሐተታ ፣ አክብር አባከ ወእመከ ይል የለም ቢሉ ። ይህን ቃሉ ካልተማሩ አያውቁትምና ። አንድም ከአክብሮተ አብ ወእም አክብሮተ እግዚአብሔር እንዲበልጥ ለማጠየቅ ። አባትን የሚረዳው ልጅ የሚረዳበት ገንዘብ ያለ እንደሆነ ትቶ መሄድ ይገባል ። የሚረዳው ልጅ የሚረዳበት ገንዘብ የሌለው እንደሆነ ትቶ መሄድ አይገባም እሱን ግን ምስለ አሳቡ ብሎ በማርቆስ ያቀናዋል ገንዘብ ያለው ነው ።

በእንተ ቀዳማዊ ስብከቱ ወመንክራቲሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፳፫ ወአንሶሰወ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ኵሉ ገሊላ እንዘ ይሜህር በምኩራባቲሆሙ ።

፳፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምኵራብ ገብቶ ሲያስተምር በገሊላ ሲመላለስ ኖረ ።
ወይሰብክ ወንጌለ መንግሥት ፣ ጌትነቱን የምትናገር ወንጌልን እያስተማረ ኖረ ። ሐተታ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር እንደነገሠ ዲያብሎስ እንደተሻረ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደጠፋ ትናገራለችና ወንጌለ መንግሥት ይላታል ወይፌውስ ኵሎ ድውያነ ወኵሎ ሕሙማነ ዘውስተ ሕዝብ ለዚህም ምልክት ቢሕዝቡ ዘንድ ያሉ ድውያንን ሁሉ ይፈውስ ነበረ ።

፳፬ ወወፅአ ስሙዓቱ ነገሩ ውስተ ኵሉ ሶርያ

፳፬ የተአምራቱ ዜና በሶርያ በ፩ቱ መዓዝን ትንገረ ።

ወአምጽኡ ኀቤሁ ኵሎ ድውያነ ወኵሎ ሕሙማነ ዘለለዚአሁ ሕማሞሙ ።
ደዌያቸው ልዩ ልዩ የሚሆን ድውያንን ወደሱ ይዘው መጡ ወጺዑራነ፤ ወእለሂ ቦሙ አጋንንት ።
የተጨነቁትን ። አጋንንት ያደሩባቸውን ። ወወርኃውያነ ፤ ሠርቀ ወርኅ እያየ የሚጥላቸውን ፣ ጨረቃ አንጂ ባታመልኩ ነው ለሚለት ፤ አንድም ምልአተ ወርኅ ሲሆን ደም ይመላል ብርድ ብርድ ይላል ደዌ ይቀሰቅሳልና ።
ወእለሂ ነገርጋር ።

ድልስጣ የሚባል ጋኔን አለ አንድ እግሩን ወደ ላይ አንድ እግሩን ወደታች አድርጎ ሲታያቸው ይጥላቸዋልና ።
ወመፃጉዓነ ።
የጸናባቸውን ።
ወአሕየዎሙ ፤
እነዚህን ሁሉ አዳናቸው ፤

፳፭ ወተለውዎ ብዙኃን አሕዛብ እምገሊላ ወእምዓሥርቱ አህጉር ወእምኢየሩሳሌም ወእምይሁዳ ወእማዕዶተ ዮርዳኖስ ። ማር ፫ ፣ ፯ ፡ ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ።

፳፭ ካሥር አህጉር ከብዙ መንደር ተወጣጥተው አምስት ገባያ ያህል ሰዎች ተከተሉት ፣ ላንድ ሽማግሌ ዐሥር ልጆች ነበሩት እኒህ እየራሳቸው እንድ አንድ አገር አቅንተው ይኖሩ ነበርና ፣ አንድም ጲላጦስ ለቀረጥ ይመቸኝ ብሎ አንዱን ከተማ ካሥር ከፍሎታል ፡ ከዚህ ተወጻጽተው ተከትለውታል እነዚህም ስለ አምስት ነገር ይከተሉታል ፡ አንዱ ገባያ መልኩን እናያለን ብለው ፣ አንዱ ገበያ ኅብስት አበርክቶ ያበላናል ብለው ፤ አንዱ ገባያ ትምርቱን እንሰማለን ብለው ፣ አንዱ ገባያ ከደዌያችን ይፈውሰናል ብለው ፤ አንዱ ገባያ የኦሪትን መፍረሻ የወንጌልን መታነጫ እናያለን ብለው ነው ። ለኒህም ትንቢት ተነግሮላቸዋል ተነግሮባቸዋል ። መልኩን እናያለን ላሉት ይሜኒ ላህዩ እምውሉደ ዕጓለ እመሕያው ተብሎ ፤ ኅብስት አበርክቶ ይመግበናል ላሉት ወኢያኅጥአሙ እምዘፈቀዱ ተብሎ ፡ ያስተምረናል ላሉት ጥዑም ለጉርዔየ ነቢብከ ተብሎ ። ከደዌያችን ይፈውሰናል ላሉት ነሥአ ደዌነ ወጾረሕማመነ ተብሎ

የአሪትን መፍረሻ የወንጌልን መታነጫ እናያለን ባሉት ቅንዓት እንዘም ለሕዝብ አብዳን ተብሎ ተነግሮባቸዋል ። እኒህንም ባምስት ነገር ይፈውሳቸዋል በሐልዮ በነቢብ በገቢር በዘፈረ ልብስ በወራቀ ምራቅ ገቢር ከሁሉ ይገባል ።

በእንተ ብፁዓን ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ወርእዮ ብዙኃነ አሕዛበ ዐርገ ውስተ ደብር ወነበረ ።

፪ ወሶበ ርእየ ይላል ፡ ብዙ ሰዎችን ባየ ጊዜ ከተራራ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ ። ሐተታ ፡ ምነው አሕዛብ አላቸው እስራኤል አይደሉም ቢሉ ብዛታቸውን ቢያይ ፡ አንድም ግብረ አሕዛብን ይሠራሉና ወደፍ የገባ ሰው ቢበዛ ከመርከብ ከተራራ ሁኖ ማስተማር ልማድ ነው ። መምህር ክፍ ካለ ቦታ ሰማዕያን ዝቅ ካለ ቦታ የሆኑ እንደሆነ ትምህርት ለሰማዕያን ይረዳልና ፡ ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ እንዲል ። አንድም በደብረ ሲና ሕገ ኦሪትን የሠራሁ እኔ ነኝ ሲል ። አንድም ልዑለ ባሕርይ ነኝ ሲል ። አንድም የመሠራሁላችሁ ሕግ ልዕልት ናት ። እናንተም ሉዓላውያን ናችሁ ሲል ።

ወቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ ። ደቀ መዛሙርቱ ወደሱ ቀረቡ ። የቀረበው ግን የራቀውም ርቆ የቀረበውም ቀርቦ ይሰማል እኒህ ግን መደበኞች ናቸውና ትምህርት የሚቀር በኒህ ነውና፣ አንድም ለጉባኤው ምፍራ አለውና ፤ ጥንተ ቀራቦች ናቸውና ቀረቡ ።

፫ ወከሠተ አፉሁ ።

፫ ነገር ጀመረ ፤ ወከሠተ አፉሁ ኢዮብ ወረገመ ለዕለተ እንተ ባቲ ተወልደ ። ወከሠተ አፉሁ ጴጥሮስ ወአኀዘ ይንግሮሙ እምቀንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ። ወከሠተ አፉሁ ፊልጶስ ወአኀዘ ይንግሮሙ በውእቱ መጽሐፍ እንዲል ።
ወመሀሮሙ እንዘ ይብል ።

እንዲህ ብሎ አስተማራቸው ፤ ሐተታ እስከ አሁን ያምስት ገብያ ሰው ይከተለው ነበር ከእንግዲህ ወዲህ በብፁዓን ዓዋጅ ይለያቸዋል ። ንጉሥ መንግሥቱ እስኪደላደልለት ድረስ ሌባ ወምበዴ ይከተለዋል ። መንግሥቱ ግን ከተደላደለ በኋላ ሌባ ወንበዴ ተለይ ብሎ ዓዋጅ እንዲነግር ፡ በብፁዓን ዓዋጅ ይለያቸዋል

፫ ብፁዓን ነዳያን በመንፈስ ። ሉቃ ፮ ፡ ፳ ። ብፁዓን እለ ያነድዩ ርእሶሙ ይላል ።

፫ አውቀው ከብዕል ነዳያን ነን የሚሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ ብዕል እንጂ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው ለኛስ ባሕርይ የሚስማማው ንዴት ነው ብለው ብዕሉም እንደ ኢዮብ እንደ አብርሃም ነው አንድም ከጥበብ ነዳያን ነን የሚሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ጥበብ እንጂ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው ለኛስ ባሕርይ የሚስማማው ድንቁርና ነው ብለው ጥበቡም እንደ ሲራክ እንደ ሰሎሞን ነው ። አንድም ከአእምሮ ነዳያን ነን የሚሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው መኰንን ተሰሎንቄ አፈወርቅን እንደጠየቀው ፡ ቅዱሳን ከበቁ በኋላ ከአእምሮ ነዳያን ነን ማለታቸው እንደምነው አለው ፡ አንተ በሀገርህ እንደምን ትኖራለህ አለው ፡ ከሁሉ በላይ ነኝ አለው ። እልፍ ብለህ በቂሳርያስ አለው የምበልጣቸውም አሉ ፡ የሚተካከሉኝም አሉ አለው ። እልፍ ብለህ ባ ቁስጥንጥንያ አለው የሚበልጡኝም አሉ የምተካከላቸውም አሉ አለው ። ዝቅ እያለ ሄደ ። እልፍ ብለህ በአንጾኪያስ አለው ። ከዚያስ እንዳለሁም እንደ ሌላሁም የሚያውቀኝ የለም አለው ። ቅዱሳንም ከአእምሮ ነዳያን ነን ማለታቸው በበላያቸው ያለውን እያዩ ነው ብሎታል ። አንድም በመማር በማርስተማር በምናኔ በንስሐ በሃይማኖት ነዳያን ነን የሚሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው እስመ ሎሙ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት ።

መንግሥተ ሰማያት የሳቸው ናትና ማለት መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉና ፡

፬ ብፁዓን እለ ይላህዉ ይእዜ ።

፬ መዝ ፴፮፡፲፭ ዛሬ የሚያዝኑ የሚያለቅሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። ሐተታ ፡ የሚገባ ኃዘን የማይገባ ኃዘን አለ ። የማይገባ ኃዘን እናት አባት ሞተብኝ እኅት ወንድም ዘመድ የለኝ ርስት ጉልት ሄደብኝ ብሎ ማዘን አይገባም ። እንዳባት እንደናት ሥላሴ እንደ ወንድም እንደ እኅት መላእክት አሉና እንደ ርስት እንደ ጉልት የማታልፍ ርስት ጉልት መንግሥተ ሰማይ አለተና ፡ የሚገባ ኃዘን የራሱን ኃጢአት አስቦ የባልንጀራውን ኃጢአት አይቶ ግፍዓ ሰማዕታትን ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን አስቦ ማዘን ይገባል ። የራስን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን እንደ አዳም እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ዳዊት ነው ፡ መልካቸው ሳይለወጥ ሳይሰቀቁ ዕንባቸው እንደ ሰንወኃ ይወርድ ነበር ። የባልደራውን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን እንደ ሳሙኤል ነው እስከ ማዕዜኑ ትላሁዎ ሳሙኤል ለሳኦል እስመ አነ መነንክዎ ወገደፍክዎ ። ወሶበ ርእያ ለሀገር በከየ ላዕሌሃ ወሶበ ርእየ ለዘያገብእ ተሀውከ በመንፈሱ እንዲል ፡ ግፍዓ ሰማዕታትን አስቦ ማዘን እንደ እስጢፋኖስ ። ወለእስጢፋኖስሰ ነሥእዎ ዕደው ጻድቃን ወቀበርዎ ወለሀውዎ ዓቢየ ላሐ እንዲል ። ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን አስቦ ማዘን እንደ ዮሐንስ ነው የዕለተ ዓርብ መከራውን እያሰበ ፸ ዘመን ቈጽሬ ገጽ ሁኖ ኑሯል ። አንድም ዛሬ በንስሐ የሚያለቅሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እስመ እሙንቱ ይትፌሥሑ ፤ የኃዘን አጸፋው ደስታ ነውና ይትፌሣሐሉ አለ እንጂ መንግሥተ ሰማይን ይወርሳሉና ሲል ነው ።

፭ ብፁዓን የዋሀን ፤

፭ ኢሳ ፲፩፥፬ ኃደግያን በቀል የሆኑ ከየውሃት ጠባይዓዊ የደረሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። አንድም ሰውነታችንን መክረን አስተምረን ማኖር እንደምን ይቻለናል ብለው በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖሩ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው እስመ እሙንቱ ይወርስዋ ለምድር ።

ምድር መንግሥተ ሰማይን ይወርሳሉና ። ሐተታ ምድር አላት ይሀ አልፎ በዚህ የምትተካ ስለሆነች ምድራውያን ጻድቃን የሚወርሷት ስለሆነ ። በምድር በሠሩት ሥራ የምትወረስ ስለሆነች ፤ በምድር ተድላ ሥጋ እንዲፈጸም ። በመንግሥተ ሰማይም ተድላ ነፍስ ይፈጸማልና ፤ ወሥርዓተ እግዚእነስ አሰፈወነ በብሂሎቱ ብፁዓን የዋሀን እስመ እሙንቱ ይወርስዋ ለምድር ከመ ሎሙ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት እንዲል ።

፮ ብፁዓን እለ ይርኅቡ ወይጸምዑ በእንተ ጽድቅ ።

፮ አብዝተንማ ከተመገብን ሰውነታችንን ወስኖ ገቶ ማኖር እንደምን ይቻለናል ብለው ከሚበሉት ከሚጠጡት ከፍለው የሚራቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እስመ ሁሉ ዘያነዲ ርእሶ እምነ መባልዕት ብዙኃት ውእቱ ይክል አኀዞተ ሥጋሁ እንዲል ፤ አንድም ጨርሰንማከተመገብነ መንግሥተ ሰማያትን በምን እንዋጃታለን ብለው ከፍለው ለነዳያን ሰጥተው የሚራቡ የሚጸሙ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ አንድም ከመብልዓ ኃጢአት የሚራቡ ከስቴ ኃጢአት የሚጸሙ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ አንድም ለፍቅሩ የሚሳሱ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። ጸምዓት ነፍስየ ለከ እንዲል ፤ አንድም በመማር በማስተማር በሃይማኖት በምናኔ በንስሐ የሚራቡ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እስመ እሙንቱ ይጸግቡ ። የረኃብ አጸፋው ጽጋብ ነውና ይጸግቡ አለ እንጂ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉና ሲል ነው ይጸምዑ ባለው ፀጸፋ ይረውዩ የሚል ይገኛል ።

፯ ብፁዓን መሀርያን ፤

፯ ለሰው የሚያዝኑ የሚራሩ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። ሐተታ ምሕረት ሥጋዊ ምሕረት መንፈሳዊ ምሕረት ነፍሳዊ አለ ምሕረት ሥጋዊ ቀዶ ማልበስ ቆርሶ ማጉረስ ቢበድሉ ማሩኝታ ቢበደሉ ይቅርታ ነው ምሕረት መንፈሳዊ ፥ ክፉው ምግባር በጐ ምግባር መስሎት ይዞ ሲኖር መክሮ አስተምሮ ክፉውን ምግባር አስትቶ በጐውን ምግባር ማሠራት ነው ምሕረት ነፍሳዊ ክፉው ሃይማኖት በጐ ሃይማኖት መስሎት ይዞት ሲኖር ክፉውን ሃይማኖት አስትቶ በጎውን ሃይማኖት ማስያዝ ነው ፤ አንድም ምሕረት ሥጋዊ አይለወጥም ምሕረት መንፈሳዊ ክፉውን ሃይማኖት ክፉውን ምግባር በጎ ምግባር ሃይማኖት መስሎት ይዞት ሲኖር መክሮ አስተምሮ ክፉውን ሃይማኖት አስትቶ በጎውን ማስያዝ ክፉውን ምግባር አስትቶ በጎውን ማሠራት ነው ። ምሕረት ነፍሳዊ መጥዎተ ርእስ ነው ። ታሪክ እንደ አንጢላርዮስ እንደ እሁ ቅዱስ ይሀ አንጢላርዮስ ባለጸጋ ነው ንፉግ ነው ፤ ነዳያን ሲያልፍ አይተው ይሀ ጽኑ ጨካኝ ባለጸጋ ለሰው አያዝንም አሉ አንዱ እኔ ሄጄ ሰጥቶኝ በልቼ ብመጣስ ባትመጣስ ተወራርዶ ሂዷል ምግቡን አቅርቦ እጁን ታጥቦ በሚመገብበት ጊዜ ስመ እግዚአብሔር ጠራበት እንዳ ይሰጠው ተርቧል እንዳይነግሠው ስመ እግዚአብሔር ጠራበት ተናዶ ዳቦውን ወርውሮ ግንባሩን ገመሰው ደሙን አብሶ ዳቦውን ጎርሶ ለምልክት ጥቂት ይዞ ሄደ ። በዚህ ሌሊት ራእይ ያያል ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ መላእክተ ጽልመት እያዳፉት ይዘዋት ሲሄዱ መላእክተ ብርሃን ሲከተሏት እናንተ ከዚህ ምን አላችሁ ሲሏቸው ምነው ትላንት ለድኃ ሰጥቶ የለም ይሏቸዋል መታው እንጂ መቼ ሰጠው አላቸው ይመስክር ተብሎ መጥተው መስክር አሉት አ ባዕል ትማልም ዘአጽገብከኒ እምጽእኩከ ዝየ ወኢተዓውቀኒ ደም እምጽንዓ ረኃብ ብሎ መስክሮ ሲያስለቅቃት መላእክተ ብርሃን እጅ ሲያደርጓት አየ ፤ ሲነጋ በዚህ ዓለም ሳሉ በገንዘብ ቢያውቁበት እንዲህ ያለ ጥቅም አለን ብሎ ነዳያንን ሰብስቦ ያለ ገንዘቡን ጨርሶ መጽውቶ ሲሄድ ነዳያን ከመንገድ አገኙት ገንዘብ ትሰጣለህ ቢሉን መጥተን ነበር አሉት ቀደም ብላችሁ መጥታችሁ ቢሆን ከፍየ እሰጣችሁ ነበረ አሁንማ ጨርሻለሁ አላቸው ፤ እንደምን አንሁን አሉት እኔን ሽጣችሁ ተካፈሉ አላቸው ለ፴ ወቄት ሸጠውታል ፤ ከተሸጠበት አገር ከብት ያውላል ማታ የሚያልበው ደም ይሆናል በዚህ ሰው እጅ ለመረዳት አልቢቃችሁም ለማለት ሲያርስ ውሎ ማታ ሣሩን አለምልሞ ውኃውን አፍልቆ ይመግባቸዋል በዚህ ዕጹብ ዕጹብ ሲሉ ከተወለደ ጀምሮ ተናግሮ የማያውቅ ድዳ ሰምቶ የማያውቅ ደንቆሮ ነበር አፍ ቢለው ድዳው ተናግሯል ደንቆሮው ሰምቷል በዚህ ዕጹብ ዕጹብ ሲሉ ተሰውሯል ።

እኁ ቅዱስ በአሕዛብና በክርስቲያን መካከል ባለች በወሰን አገር ኤጲስቆጶስነት ተሹሞ ይኖራል። አሕዛብ ክርስቲያንን እየማረኩ ሲወስዱ ገንዘብ

እየሰጠ ይመልሳቸዋል እንዲት ድኃ ልጇዋ ተማሬ ከባት መዋታ ገንዘብ ሰጠኝ አለችው ገንዘቤን ጨርሻለሁ እኔን ተከተሽ ልጅሽን መልሺ አላት ። እሱን ተከታ ልጇዋን መልሳለች ከሄደበት አገር የንጉሡ ልጅ ሞተችበት ኃዘን እንደጸናበት አይቶ ልጅህን ባነሣልህ ምን ባደረግህልኝ አለው የመንግሥቴንም እኩሌታ ቢሆን እሰጥሃለሁ አለው ይህንንስ አልሻም ከኔም አስቀድሞ ከኔም በኋላ የተማረኩትን ክርስቲያን ትሰጠኝ እንደሆነ ሳሥነሳልህ አለው ፤ ይሁንልህ አለው እሥነሥቶት ከሱም አስቀድሞ ከሱም በኋላ የተማረኩትን ክርስቲያን ይዞ ወጥቷል ፤ በዚህም ጌታን መስሎታል ጌታ እሱ ሰው ሳይሆን ከሱ አስቀድሞ የነበሩትን ሰው ከሆነም በኋላ ቢአል የወረዱትን ፩ድ ቀን በዕለተ ዓርብ ይዞ ስመውጣቱ ምሳሌ አንድም በንስሐ ለሰው የሚያዝኑ ቀሳውስት ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እስመ ሎሙ ይምህርዎሙ ፤

ለሳቸውም ሥሳሴ ያዝኑላቸዋል ይራሩላቸዋልና ።

፰ ብፁዓን ንጹሐን ልብ ፤ መዝ፡ ፳፫ ፤ ፬ ።

፰ ከንጹሐን ልቡና የደረሱ አንድም በንስሐ ከኃጢአት ንጹሐን የሆኑ ፣ አንድም ከቂም ከበቀል ንጹሐን የሆኑ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ እስመ ዘያነብር ቂመ ውስተ ልቡ ኢውክፍት ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር ጸሎቱ ለመስተቀይም ከመ ዘርዕ ዘወድቀ ማእከለ አሰዋክ እንዲል ።
እስመ እሙንቱ ይሬእይዎ ለእግዚአብሔር ።
ሰውነታቸው ጸርቶላቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና እስመ በእንጽሖ መንፈስ ርእይዎ ነቢያት ለእግዚአብሔር ወተናጸሩ ገጸ በገጽ እንዲል ። እስካሁን ይሬእይዎ አላለ አሁን ይሬእይዎ አለ ምነው ቢሉ በኒህ ማየት የሁሉን መናገር ነው ።

፱ ብፁዓን ገባርያነ ሰላም ።

፱ እብነት እለ ይገብሩ ሰላመ ይላል ፤ አቀበቱን ወጥተው ቍልቍለቱን ወርደው ሰውን ከሰው ጋራ የሚያስታርቁ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ እንደ መልከ ጼዴቅ እንደ ሊቀ ሀገር የመልከ ጼዴቅ በጳውሎስ ታውቋል፤ ሊቀ ሀገር ሦስት ልጆች ነበሩት።አንተ ይህን ሥራ አንተ ይህን ሥራ ብሎ አዝዞ እሱማን ከማን ተጣልቷል እያለ እየዞረ ሲያስታርቅ ይውል ነበር ። አንድም ሰው ሰርቆ ቀምቶ ከፈጣሪው ጋራ የሚጣላ የሚበላው የሚለብሰው እንጂ ቢያጣ ነው ብለው የሚበላውን የሚለብሰውን ሰጥተው ከእግዚአብሔር ጋራ የሚያስታርቁ ባለጠጎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው አንድም ሰውን በንስሐ ከእግዚአብሔር ጋራ የሚያስታርቁ ቀሳውስት ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። እስመ እሙንቱ ውሉደ እግዚአብሔር ይሰመዩ ፣

የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና እስካሁን ውሉደ እግዚአብሔር አላለም አሁን እንዲህ ማለቱ ስለምን ቢሉ በመሰሉት ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ ወደ መቃብር ወርዶ ሰውን ከእግዚአብሔር እንዳስታረቀ እሳቸውም አቀበቱን ወጥተው ቍልቍለቱን ወርደው በማስታረቃቸው ይመስሉታልና በኒህ መምሰል የሁሉንም መምሰል መናገር ነው ።

፲ ብፁዓን እለ ይሰደዱ በእንተ ጽድቅ። ፩፡ጴጥ፡ ፪ ፡ ፳
፫ ፡ ፲፬ ፬ ፡ ፲፬

፲ በመማር በማስተማር በምናኔ በንስሐ በሃይማኖት አገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። እስመ ሎሙ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት

መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉና ፡ በመጀመሪያ ተናግሯት ውስጥ ለውስጥ ሲናገራት መጥቶ ነበርና በ፰ኛው አነሣት በመጀመሪያ ማንሣቱ ለአዳም እንደ ተሰጠች ለማጠየቅ በ፰ኛው ማንሣቱ በ፰ኛው ሽህ ለሁሉ እንድትሰጥ ለማጠየቅ ።

፲፩ ብፁዓን አንትሙ ሶበ ይሰድዱከሙ ።

፲፩ ከሀገራችሁ አስወጥተው ቢሰዷችሁ ንዑዳን ክቡራን ናችሁ ወይዘነጕጕከሙ ።
ዓብዳን ዝንጉዓን ጊጉያን ርጉማን ስሑታን ቢሏችሁ ወይነቡ ኵሎ እኩየ ላዕሌከሙ እንዘ ይሔስው በእንቲአየ ።
በኔ ስም ስላመናችሁ በኔ ስም ስለተጠራችሁ በኔ ስም ስላስተማራችሁ ፣ በሐሰት ክፉውን ነገር ቢናገሩባችሁ ።

፲፪ ተፈሥሑ ወተሐሠዩ ።

፲፪ ፈጽሞ ደስ ይበላችሁ ።

እስመ ብዙኅ እሤትክሙ በሰማያት ።
ዋጋችሁ በኔ ዘንድ ፍጹም ነውና ካሥሩ ቃላት አንጸጽሮ ዐሥሩን ብፁዓን ተናገረ ዐሥረኛውን በዮሐንስ ያመጣዋል ። ሙሴ ዘጠኙን ቃላት በአሪት ዘፀአት ተናግሮ ዐሥረኛውን በአሪት ዘሌዋውያን እንዳመጣው ።
እስመ ከማሁ ሰደድዎሙ ለነቢያት እለ እምቅድሜከሙ ።
ከናንተ አስቀድሞ የነበሩ ነቢያትን ከሀገራቸው አስወጥተው ይሰዷቸው ነበርና ፤ ይሰድዱከሙ ሻለው አንድም መከራስ እንቀበል ብንል ማን እብነት ይሆነናል ትሉኝ እንደሆነ ከናንተ አስቀድሞ የነበሩ ነቢያትንም እንጂ ነቢያትንም እኮን ከሀገራቸው አስወጥተው ይሰዷቸው ነበር ፣ እኒያ እብነት ይሁኗችሁ ።

በእንተ ሐዲስ ኪዳን ተአርዮታ ምስለ ብሊት ፣

፲፫ አንትሙ ውእቱ ጼው ለምድር ማር ፱ ፶ ሉቃ ፲፬ ፡ ፴፬ ።

፲፫ በዚያውም ላይ የሰው አብነቱ እናንተ ናችሁ ወእመሰ ጼው ለሰሐ በምንት እንከ ይቄስምዎ ።

ጨው ጣዕም ባይኖረው በምን ያጣፍጡታል ፣ ራሱን እንድም አፍርጁን ሽንኩርቱን በምን ያጣፍጡታል ፤ አልቦኬ እንከ ዘይበቍዕ ።

የሚረባው የሚጠቅመው የለም ለአፍርጁ ለሽንኩርቱ ፣ እንድም ለራሱ የሚያገኘው ረብሕ ጥቅም የለውም ።

ዘእንበለ ዘይገድፍዎ አፍአ ።
አፍአ አውጥተው ይጥሉታል ወይከይድዎ ሰብእ በእግረሆሙ ሰዎች በእግራቸው ይጠቀጥቁታል እንጂ ፤ ሐተታ ቢከቡት ይናዳል ቢንተራሱት ራስ ይመልጣል ከተክል ቦታ ቢያደርጉት ተክል ያደርቃል ብለው እንድም አንትሙ ውእቱ ጼው ለምድር የሰው አብነት እናንተ ናችሁ ፣ እናንተ አብነት ካልሆናችሁ ማን አብነት ይሆንላችኋል ፣ እንድም ለሕዝቡ እናንተ አብነት ካልሆናችኋቸው ማን አብነት ይሆናቸዋል ። ለሕዝቡ የምትረቧቸው የምትጠቅሟቸው የለም ። እንድም ለራሳችሁ የምታገኙት ረብሕ ጥቅም የለም ። ዘእንበለ ዘይገድፍዎ አፍአ ፣ ሕዝቡ ከልቡናቸው በአፍአ ያወጥዋችኋል ፣ ወይከይድዎ ። በልቡናቸው ይንቅፉችኋል እንጂ ። እንድም ሥላሴ ከመንግሥተ ሰማይ አፍአ ወደምትሆን ወደ ገሃነም ያወጧችኋል እንጂ ፤ ወይከይድዎ ፣ አጋንንትም መከራ ያጸኑባችኋል እንጂ ። በማደሪያቸው ሰብእ አላቸው ። እንድም በቂሙ ሰዎች ይጠቀጥቋችኋል ቅዱስ ጊዮርጊስ እንዳስነሣው ፍቁራ አስንሥቶ ወዴት ነበርህ ቢለው ከኤጲስ ቆጶሳችሁ ላይ ነበርሁ ብሏል

፲፬ አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ።

፲፬ አብነትነታቸው በብዙ ወገን ነውና ደገመው ፤ የሰው አብነቱ እናንተ ናችሁ ።
ኢትክል ተከብቶ ሀገር እንተ ተሐንጸት መልዕልተ ደብር ፣ ከተራራ ላይ የተሠራች መንደር መሰወር አይቻላትም ።

፲፭ ወኢየኀትው ማኅቶተ ከመ ያንብርዋ ታሕተ ከፈር ። ማር ፬ ፡ ፳፩ ፡ ሉቃ ፡ ፰ ፡ ፲፮ ።

፲፭ አንቅብ ቅርጫት ሊደፉባት መቅረዝ የሚያበራ የለም ። አላ ያነብርዋ ዲበ ተቅዋማ ወታበርህ ለኵሉ እለ ውስተ ቤት ከመቅረዝ ላይ አኑረዋት ከቤት ላሉ ሁሉ ታበራ ዘንድ ነው እንጂ ።

፲፮ ከማሁ ይብራህ ብርሃንክሙ በቅድመ ሰብእ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።

፲፮ እንዲህም ሁሉ ሥራችሁ በሰው ፊት ይሁን ከመ ይርአዩ ምግባሪክሙ ሠናየ ወይሰብሕዎ ለአቡክሙ ዘበሰማያት ።

በጐ ሥራችሁን አይተው ሰማያዊ አባታችሁን ያመሰግኑት ዘንድ እንዲህ ያሉ የትሩፋት አበጋዝ ያልነሣልን ብለው ፣ ሐተታ ፣ ምነው በሚያመጣው ጸሊ በኅቡእ ይል የለም ቢሉ አብነት የሚሆኑበትን ተገልጸው ይሠሩታል አብነት የማይሆኑበትን ተሰውረው ይሠሩታልና እንዲህ አለ ፤ እንድም በተራራ ላይ የታነጸች መንደር ልሰወር ብትል መሰወር እንዳይቻላት የተራራው ከፍታ እንዲገልጻት ። በመቅረዝ ላይ ያለች ፋና ልሰወር ብትል መሰወር እንዳይቻላት የመቅረዙ ከፍታ እንዲገልጻት ፤ እናንተም ሥራውን አብዝታችሁ ሥሩት ግድ በተአምራት ይገልጻችኋል ሲል ነው ። ደብር ተቅዋም አንድ ወገን ሀገር ማኅቶት አንድ ወገን ፣ ደብር ተቅዋም ሥጋ ሀገር ማኅቶት ነፍስ ፣ ከሥጋ ጋራ የተዋሐደች ነፍስ ሥራ ሠርታ ልትገለጽ ነው እንጂ ፣ ተሰውራ ልትቀር አይደለም እንድም ደብር ተቅዋም ሰውነት ሀገር ማኅቶት አእምሮ ጠባይዕ በሰውነት ያለ አእምሮ ጠባይዕ ሥራ ሠርቶ ሊገለጽ ነው እንጂ ተሰውሮ ሊቀር አይደለም እንድም ደብር ተቅዋም ሥጋ ሀገር ማኅቶት መለኮት ከሥጋ ጋራ የተዋሐደ መለኮት አስተምሮ ታምራት አድርጐ አምላክነቱን ሊገልጽ ነው እንጂ ፣ ተሰውሮ ሊቀር አይደለም ። እንድም ደብር ተቅዋም መስቀል ሀገር ማኅቶት ጌታ በመስቀል የተሰቀለ ጌታ ሙቶ ተነሥቶ አምላክነቱን ሊገልጽ ነው እንጂ ሙቶ ሊቀር አይደለም ፣ እንድም ደብር ተቅዋም ኦሪት ሀገር ማኅቶት ወንጌል በኦሪት ላይ የተሠራች ወንጌል ባደባባይ ተገልጻ ልትነገር ነው እንጂ ። ተሰውራ ልትቀር አይደለም ። እንድም ደብር ተቅዋም ሕዝቡ ሀገር ማኅቶት ኤጲስ ቆጶስ በሕዝቡ ላይ የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ካደባባይ ወጥቶ ጉባኤ ሰርቶ ሕዝቡን ሊያስተምር ነው እንጂ ፣ ባዳራሽ ገብቶ አልፍኝ ተከቶ ተሰውሮ ቢባላ ሲጠጣ ሊውል አይደለም

፲፯ ኢይምሰልክሙ ዘመጻእኩ እስዕሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት ፣ ብፁዓን ብፁዓን እያለ ሲያስተምር ሰምተው ኦሪትን ነቢያትን እንጂ ሊያሳልፋቸው መጥቷል እንዲሉት ዐውቆ አመጣ ። እንዲሉትም ዐውቆ ማምጣት ልማድ ነው ። ትውልደ አራዊተ ምድር ቢሏቸው አብርሃምን ያህል አባት ሳለን ትውልደ አራዊተ ምድር ይለናል እንዲሉት ዐውቆ ኢይምሰልክሙ ዘታመስጡ በብሂለ አብ ብነ አብርሃም እንዳለ ፣ ወኢትሁቦ ለጻድቅከ ይርአይ ሙስና ሙስና ቢሏቸው ይህንማ ዳዊት ለራሱ የተናገረው አይደለም እንዲሉት ዐውቆ ታበውሑነሁ እሰብእ ንንግርክሙ ከሡተ በእንተ ዳዊት ርእሰ አበው ከመ ሞተ ወተቀብረ ወኀቤነ ሀሎ መቃብሪሁ እስከ ዮም እንዳለ ፣ ከዚህም እንዲህ አለ ፤

፲፯ ኦሪትን ነቢያትን ላሳልፋቸው የመጣሁ አይምሰላችሁ ኢመጻኩ ይላል ፡ ላሳልፋቸው አል መጣሁም ።

ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ አፈጽሞሙ ።
ፍጹማን ላደርጋቸው ነው እንጂ ፤ ኢትቅትልን በኢታምዕዕ ኢትፍቱን በዘርእያ ላጸናቸው ነው እንጂ ወፈጸመ ሕገርትዕ በሕገ ትሩፋት እንዲል ።

፲፰ አማን አማን እብለከሙ እስከ አመ የሐልፍ ሰማይ ወምድር የውጣ እንተ አሐቲ ኅርመታ ወአ ሐቲ ቅርጸታ ኢተሐልፍ እምኦሪት ወአምነቢያት እስከ ሶበ ኵሉ ይትገበር ወይከውን ። ሉቃ፡፲፮፡፲፯ ።

፲፰ ሰማይ ምድር አስኪያልፍ ይህ ሁሉ እስኪ ሆን ይህ ሁሉ እስኪደረግ ድረስ ሥርዓቷ ጽፈቷ አን ዲት የምትሆን ኢትፍቱስ እንኳ ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ አታልፍም ብዩ እንዳታልፍ በውነት እነግ ራችኋለሁ የድ ለአሌፍ ዐሥረኛ እንደ ሆነ ኢትፍ ቱም ለኢታምዕዕ ዐሥረኛ ናትና ። አንድም አሰራ ረዟ አቀራረጹዋ አንድ የምትሆን ዐሥርቱ ቃላት ሁሉ ሲያልፍ ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ እንዳታልፍ አታልፍም ብዩ በውነት እነግራችኋለሁ ፡ በሀገራ ቸው ፲ቱ ሲሉ የውጣ ይላሉ አንዲት ጭራ ናት ዕዝል ቅጽል የላትም ። በኛም ፲ አንዲት ጭራ ናት ዕዝል ቅጥል የላትም ። አንድም ለኛ ፊደል ዐሥረኛው ተ ነው፡መስቀላዊት ሕገ ክርስቶስ ወንጌል ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ ወደሰው ልቡና አትገባም ብዩ እነግራችኋለሁ ። ወኅለፈት ሰንበት እንዲል ፡ አብራ ትነገራለች እንጂ ማለት ነው ፤ ውኅጣ የሚል አብ ነት ይገኛል ። የውጣ ማሰት ነው ። በዳር ሮ ሎ ብሎ ይገኛል ፡ ሮ ቢል ከመንግሥተ ሮም የምትበልጥ ሎ ቢል ልዕልት የምትሆን ወንጌል ከኦሪት ከነቢ ያት ተለይታ ወደሰው ልቡና አትገባም ብዩ እን ዳትገባ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፲፱ ዘኬ ፈትሐ እሐተ እምእላ ትእዛዛት እንተ ተሐጽጽ ወይሜህር ከመዝ ለሰብእ ሕጹጸ ይከውን በመንግሥተ ሰማያት ። ያዕ፡ ፪ ፡ ፲ ።

፲፱ ካ፲ቱ ቃላት አንዲቱ ታናሽ ናት ብሎ ለራሱ የሚሠራ ለሌላው የሚያስተምር ውፁእ ሲል ነው ከመንግሥተ ሰማያት የወጣ ይሆናል ፡ መኑ አብእ ለዘ እግዚአብሔር አሕጻጸ ወሐጽ መንፈቅ ወየሐጽጾሙ እመንግሥተ አቡሁ እንዲል ፤ ወዘሰ ይገብር ወይሜህር ከመዝ ለሰብእ ውእቱ ዐቢየ ይከ ውን በመንግሥተ ሰማያት፡ከዐሥርቱ ቃላት አንዲቱ ደግ ናት ብሎ ለራሱ የሚሠራ ለሌላው የሚያስተ ምር ግን ለመንግሥተ ሰማያት ባለቤት ይሆናል ። እንድም ይከውን ሕጹጸ ፡ እንደ ጨረቃ እንደ ንኡስ ኮከብ ይሆናል ፤ ይከውን ዐቢየ እንደ ፀሐይ እንደ ዐቢይ ኮከብ ይሆናል ።

፳ ናሁ እብለከሙ ከመ ለእመ ኢፈድፈደ ጽድ ቅከሙ እምጸሐፍት ወፈሪሳውያን ኢትበውኡ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፴፱ ።

፳ በቁሙ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ናቸው ብሎ ፡ ሥራችሁ ከጸሐፍት ከፈሪሳውያን ሥራ ካልበለጠ ኢያፈድፈድከሙ ጻዲቀ እብዝታችሁ ሥራ ካልሆ ራችሁ መንግሥተ ሰማያት አትገቡም ብዩ አንዳት ገቡ በውነት እነግራችኋለሁ ። እኒያም አልገቡ እና ንተም አትገቡ ማለት ነው ። አንድም ደጋጎች እለ አብርሃም እለ ሙሴ እለ ዳዊት ናቸው ብሎ ሊቁ ወስዶታል ብሎ በሥራ መበላለጥ ከሌለ በክብርም መበላለጥ የለም ብዩ በውነት እነግራችኋለሁ ። ሥራው ምንድ ነው ቢሉ አፍቅሮ ጸላዕት ተዐፍዖ መል ታሕት መንኖ ጥሪት ነው ። ይህንማ እነሱስ አድር ገውት የለም ለአመ ርኢከ እድገ ፀላዒከ ዘኃየሎ ጾሩ ኢትትዓደዎ እላ እስተልዕል ምስሌሁ እንዲል ዘፀ ፳፫፡፭ ፡ አድርገውት የለም ቢሉ መጥዎተ ርእስ ነው ይህንስ አድርገውት የሰም ሙሴ እምትጥስዮሙ ለእሉ ሕዝብከ ጠስየኒ እመጽሐፈ ሕይወትከ ብሂል ዘፀ ፴፪፡፲፩ ፡ ዳዊትስ ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ እንዘ ኖላዊሆሙ አነ ዘአበስኩ ፤ ዳዕሙ ለትረድ እዴከ ላዕሌየ ወላዕለ ቤተ አቡየ ብሎ የሰም ቢሉ ፡ እኒያ ለዘመዶቻቸው ነው ፤ እናንተ ግን ለሁሉ አድርጉት ሲል እኒያ አስበውት ቀርቷል እናንተ ግን አድርጉት ሲል ነው ፡ ዳግመኛ ሕግ ሁኖ ስላልተጻፈ ተጽፎ የለም ቢሉ ገብሩ ተብሎ ተጽፏል እንጂ ግበሩ ተብሎ ተጽፏልን ፤ በሥራም ካልተበላለጣችሁ ማለቱስ እንደ ምነው ቢሉ ለእኒያ አብነት አልነበራቸውም ለኒህ ግን እብነት ጌታ አላቸውና ፡ እኒያ በልጅነት አልታደሉም እኒህ ግን በልጅነት ታድሰዋልና ። ለኒያ አጋዥ አልነበራቸውም ለኒህ ግን አጋዥ ሥላሴ መላእክት መጻሕፍት መምራን አሏቸውና ።

፳፩ ሰማዕከሙ ዘተብህለ ለቀደምትከሙ ኢት ቅትል ነፍሰ ።

፳፩ ሰቀደሙ ሰዎች ነፍስ አትግደል የተባ ለውን ዘጸ ፳፡፲፫ ዘከመ ተብህሰ ሎሙ እንደተባለላቸው ዘይቤልዎሙ ያሏቸውን ዘከመ ይቤልዎሙ እንዳሏቸው ሰምታች ኋል ።
ወዘሰ ቀተለ ረስሐ ውእቱ ለኵነኔ ።
ነፍስ የገደለ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል
የተባለውን ሰምታችኋል ።

፳፪ ወአንሰ እብለከሙ ኵሉ ዘያምዕዕ እኅዋሁ በከንቱ ረስሐ ውእቱ ለኵነኔ ።

፳፪ እኔ ግን ወንድሙን በከንቱ ያሳዘነ ሁሉ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል ብዩ እነግራ ችኋለሁ ፤ ሐተታ ኦሪትንስ ወንጌልንስ የሠራ እሱ አይደለም እኔ ግን

ግሰቱ ሰለምን ቢሉ ጌታ ሁን እንዳሻህ ሁን እንዲሉ ይህስ በጌታ የለበትም ብሎ አሪትን በሙሴ በኢያሱ አድሮ ሠርቷታል ወንጌልን ግን እሱ ሰው ሁኖ ሠርቷታልና ፤ አንድም ለቀደሙ ሰዎች እንዲህ ብየ ነበር ዛሬ ግን እንዲህ እልሁ ። አንድም እሚሃሊ የምኒ ያን ጊዜ እንዲህ ብየ ነበር ዛሬም እንዲህ እልኩ ። በከንቱ እለ ፀ መዓት ዘበርትዕ እንዲል ፤ የሚገባ ቁጣ አለና ሕፃናት ያል ተማሩትን እንዲማሩ የተማሩትን እንዳይገድፉ መናፍቃን እንዳይሠለጥኑ ሃይማኖት እንዳይጠፋ ከሀደት እንዳይሰፋ ፣ አንድም በከንቱ ያለውን መፍ ቀርያን መዓት የጨመሩትን ነው በሐጌ መጽሐፍ ፪ ፳ ፣ ዝወርቅ ወዝ ብሩር ዘዚአየ ባለው መፍቀርያን ብሩር ወለዘፈቀድኩ እሁቦ ባለው እንደጨመሩበት ወዘሂ ይቤሎ ኅሡር ዘጸርቅ ረስሐ ።

ወንድሙን ጨርቅ ለባሽ እባተ ታናሽ ብሎ የሰደበ በደለ ፤
ወይትኴነን በዐውድ
በዐደባባይ ይፈረድበታል ።
ወዘሂ ይቤሎ ለእኁኁ ዓብድ ረስሐ ውእቱ ።
ወንድሙን ዲዳ ደንቆሮ ያለው እሱ በደለ ።
ወይትኴነን በእሳተ ገሃነም ።

በእሳተ ገሃነም ይፈረድበታል ሐተታ ወንድሙን ጨርቅ ለባሽ እባተ ታናሽ ቢለው ባደባባይ ፤ ድዳ ደንቆሮ ቢለው በገሃነም ይፈረድበታል አለ ምነው ቢሉ ፣ ከተፈጥሮተ ሥጋ ተፈጥሮተ ነፍስ እንዲበልጥ ከስድቡም ስድቧ ይበልጣልና ፣ ከፍዳውም ፍዳውን አበለጠ ፤ አንድም በዓውድ ገሃነም በገሃነም ዓውድ ያሉነው።በአክብሮዎ ፍርሀዎ በፍርሀዎ አክብሮዎ እን ዳለ ። ይህንም ሊቁ ዘሰ ፀረፈ ሳዕለ ሰብእ ጸረፈኬ ላዕለ እግዚአብሔር ብሎ ወስዶታል ። መጽሐፉን አይቶ መንቀፍ ጸሐፊውን ሕንጻውን አይቶ መንቀፍ ሐናጺውን መንቀፍ እንደሆነ ፍጥረቱንም አይቶ መንቀፍ እግዚእብሔርን መንቀፍ ነውና ።

፳፫ ወእምከመኬ ታብውእ መባዕከ ውስተ ምሥዋዕ ወበህየ ተዘከርከ ከመ ቦ እኁከ ዘተኃየሰከ ።

፳፫ መባህን ለቤተ እግዚአብሔር በምትሰጥ በት ጊዜ አንተ ወንድምህን የነቀፍህበት ፣ ዘተኃየ ሰከ እሱ አንተን የነቀፈበት ነገር እንዳለ ብታስብ ።

፳፬ ኅድግ ሀየ መባዕከ ቅድመ ምሥዋዕ ።

፳፬ መባውን ከደጅ ሰላም እኑረህ ወሑር ቅድመ ተኳነን ምስለ እኁከ ።

እስቀድመህ ከወንድምህ ተወቃቅሰህ ታረቅ ።
ወእምዝ ገቢአከ አብእ መባዓከ፣ ከዚህ በኋላ ተመል ሰህ መባህን ስጥ ። ሰጥቶ ቢሄድ መባው እንኳን የገ ባልኝ እንጂ ብሎ ዕርቁ በቀረ ነበርና ፤ ይዞ ወደ ቤቱ ተመልሶ ቢሆን ዕርቁም መባውም በቀረ ነበርና ልብ እንዲቀረው ከእዳሪ እኑራለሁ ብሎ ፈጥኖ ታርቆ እንዲመለስ እንዲህ አለ አንድም ወእምከመኬ ብለህ መልስ ጸሎት በምትጸልይበት ጊዜ የነቀፈህ ወንድ ምህ የነቀፍከው ወንድምህ እንዳለ ብታስብ ጸሎቱን ትተህ ሂድ አስቀድመህ ከወንድምህ ተወቃቅሰህ ታረቅ ከዚህ በኋላ ተመልሰህ ጸሎትህን ጸልይ ። በቂም በበቀል ሁኖ የጸለዩት አይረባም አይጠቅም ምና እስመ ዘያኀብር ቂመ ውስተ ልቡ ኢውክፍት ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር ጸሎቱ ለመስተቀይም ከመ ዘርዕ ዘወድቀ ማእከለ አሰዋክ እንዲል ።

፳፭ ኩን ጠቢበ ለዕድውከ ፍጡነ እንዘ ሀሎከ ምስሌሁ ውስተ ፍኖት ።

፳፭ በመንገድ ከሱ ጋራ ሳለህ በባላጋራህ ፈጥ ነህ ዕወቅበት ታረቅ በፍኖት ብሎ በሉቃስ ያቀና ዋል ።

ከመ ኢይመጡከ ዕድውከ ለመኰንን
ባላጋራህ ለዳኛ አሳልፎ እንዳይሰጥህ ።
ወመኰንን ይሜጥወከ ለወዓሊሁ ።
ዳኛውም አሳልፎ ለሎሌው ይሰጥሃል ።
ወወአሊሁ ይሞቅሐከ ።
ሎሌውም ያግዝሃል ።

፳፮ አማን እብለከ ከመ ኢትወፅእ እምህየ እስከ ሶበ ትሜልጥ ደኃሪተ ገመስ ዘላዕሌከ ።

፳፮ ሌላው ገንዘብህስ ይቅርና ሰንኪቶ የምት ባል ቀለበትህን እስከመስጠት ደርሰህ ፤ አንድም ገመሰ ደኃሪት ይላል ፤ የታናሽ ጣትህን ቀለበት እስከ መስጠት ደርሰህ ከግዞት ቤት አትወጣም ብየ እንዳ ትወጣ በውነት እነግርሃለሁ ። አንድም ኩን ጠቢበ ብለህ መልስ በዚህ ዓለም ሳለህ በባለጋራህ በዲያብ ሎስ ዕወቅበት ። ይህን ዓለም ፍኖት አለው በመን ገድ አንዱ ሲያልፍ አንዱ ሲተርፍ እንደሆነ በዚህም ዓለም አንዱ ሲያልፍ አንዱ ሲተርፍ ነውና ። ባለ ጋራህ ዲያብሎስ ለጌታ አሳልፎ እንዳይሰጥህ ። ጌታም አሳልፎ ለዲያብሎስ ይሰጥሃል ። ዲያብሎስ ያግዝሃል ። ወዓሊሁ አለ የግድ ነው የፈቃድ አይደ ለም ። ሥራ ሠርተህ ያገኘኸው ጸጋ ክብር ይቅርና ባርባቀን ያገኘኸውን ልጅነት እስከ ማጣት ደርሰህ ከገሃነም አትወጣም ብየ እንዳትወጣ በውነት እነግ ርሃለሁ ። አንድም ፣ በዚህ ዓለም ሳለህ በባለጋ ራህ በፈቃደ ሥጋህ ፈጥነህ ዕወቅበት ። ባላጋራህ ፈቃደ ሥጋ አስፈርዶ ለጌታ እንዳይሰጥህ ። ጌታም አሳልፎ ለዲያብሎስ ይሰጥሃል ፤ ዲያብሎስ ያግዝሃል እማን እብለከ ። በነቢብ በገቢር በሠራኸው ኃጢ አት ቀርቶ በሐልዮ በሠራኸው ኃጢአት ተፈርዶብህ ከገሃነመ እሳት አትወጣም ብየ እንዳትወጣ በውነት እነግርሃለሁ ። ከሐልዮ ኃጢአት የሚነጻ አለን ቢሉ

የሚየሲዝ ሐልዮ የሚያሲዝ ሐልዮ አለ ። የሚያሲዝ ሐልዮ አሰርቃለሁ እቀማለሁ ብሎ ሂዶ ሰው ነቅቶበት ውሻ ጩሆበት እጥር ጠንቶበት ቢመለስ ያሲዛል ፤ የማያሲዝ ሐልዮ አሰርቃለሁ እቀማለሁ ብሎ ይሄዳል ከመንገድ ሲደርስ ፈጣሪዬ ቢፈርድብኝስ ብሎ የተመለሰ እንደሆነ ይህ አያሲዝም ። አንድም ሁሉም ያሲዛል ስዚህ ቅሉ ጥቂት ቀናና ያሻዋል በሰይጣን ጻር ተወግቷልና ፥ ሁለት ሰዎች ከሰልፍ ይገባሉ ሁለቱ ሁሉ ተወግተው ይመለሳሉ አንዱ ይሞታል አንዱ ይድናል ከዳነው ላይ እትራት ይጠፋልን ፤ ይህም በአቡነ እንጦንስ ታውቋል በሚሞቱበት ጊዜ መላእክተ ጽልመት ቀረቡ መላእክተ ብርሃን መጥተው ከዚህ ሰው ምን አላችሁ አሏቸው ፤ ምነው ያስ የሐልዮው አሏቸው ከቆብ በኋላ ነው ከቆብ በፊት አሏቸው ከቆብ በፊት ነው እንጂ ከቆብ በኋላማ በእንጦንስ ምን ተገኝቶበት አሉ ። ያማ በቆብ ታርቆበት የለም ወግዱ ብለዋቸዋል ።

፳፯ ሰማዕክሙ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ ኢትዘምው ። ዘፀ ፳ ፡ ፲፬ ።

፳፯ ለቀደሙት ሰዎች አትስሰኑ የተባለውን ሰምታችኋል ።

፳፰ ወአንስ እብለክሙ ኵሉ ዘርእያ ለብእሲት ወፈተዋ ወድአ ዘመወ ባቲ በልቡ ።

፳፰ እኔ ግን ሴትን ያየ ሁሉ ፈጽሞ በደለ ብዩ እነግራችኋለሁ ርእይን መከልከሉ ነው ቢሉ አዎን አርቆ ማጠር ነው ፤ አንድም ፈተዋ ያለውን ይሻል አይቶ ባገኘኋት ቢል ።

፳፱ እመኒ ዓይንከ ዘየማን ታስሕተከ ምልሐ ወግድፋ እምላዕሌከ ማር ፱ ፡ ፵፯ ፤ ማቴ ፲፰ ፡ ፱ ።

፳፱ ቀኝ ዓይንህ ምክንያተ ስሕተት ብትሆን ብህ ካንተ አውጥተህ ጣሳት ።

እስመ ይኄይሰከ ነቋረከ ትባእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት እምትባእ ውስተ እሳተ ገሃነም ምስለ ክ፪ሆን አዕይንቲከ ፥ ዛሬ ሁለት ዓይን ኑሮህ ኋላ ገሃነም ከምትገባ በዚህ ዓለም ሳለህ ከሁለት ዓይንህ አንዱ ጠፍቶ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፤ ይህን ያደረጉ ብዙ ናቸው ከዚያው ግን ስምኦን ሰፋዬ አሣዕን ፤ አንዲት ሴት ወይዘሮ መጥታ ጫማ ስፋልኝ አለችው ሰፍቶ ሰጣት እየተመላለሰች አስችገረችው ጫማውን ነው ሰፍቸ ስጥቸሻለሁ ምን ያመሳልስሻል አላት ፥ ይህ ሁሉ ምክንያት ነው አንተን ብወድህ ነው አለችው በምን ነገር አላት ፥ መልከ መልካም ነህና አለችው ምኔ መልካም ነው ቢላት ሁለንተናህ መልካም ነው ይልቁንም በዓይንህ ይጸናብኛል አለችው ትወጅዋለሽ አላት አዎን አለችው ። ይህማ ምን ቁም ነገር አለው ውኃ አይደለም ብሎ በያዘው መንጉል አውጥቶ ሰጧታል።

፴ ወእመኒ እዴከ ዘየማን ታስሕተከ ምትራ ወግድፋ እምላዕሌከ ።

፴ ቀኝ እጅህ ምክንያተ ስሕተት ብትሆንብህ ቈርጠህ ጣሳት ። እስመ ይኄይሰከ ይታጐጐል አሐዱ እምአባልከ እምዘሎ ሥጋከ ይትወደይ ውስተ እሳተ ገሃነም ።

በዚህ ዓለም ከሕዋሳትህ አንዱ ሳይጐል ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትወርድ በዚህ ዓለም ከሕዋሳትህ አንዱ ጎድሎ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ። ይህን ያደረጉ ብዙ ናቸው ። ከዚያው ግን አባስ ካህነ ሮሜ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሀገረ እንጾኪያ ፤ አባስ ካህነ ሮሜ በተአምረ ማርያም ታውቋል አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘአንጾኪያ ቀድሞ አረማዊ ነበረ ኋላ አምኖ ተጠምቆ ተምሮ ተሾሟል በሀገራቸው የተሾመው ፯ ቀን ቀድሶ ያቈርባል በዚያ ልማድ በመስቀል እየባረከ ሲዞር ቀድሞ በአረማዊነት ሳለ በግብር የምታውቀው ሴት መለያ ይሁነኝ ብላ እጁን ነከሰችው ጦር ተነሣበት ከዚህ ሁሉ ያደረሰችኝ ይህች እጅ አይደለችም ብሎ ከዕቃ ቤት ገብቶ እጁን ቆርጦ ጣላት ፥ አባታችን ገብተህ ቀድስልን አሉት አይቻለኝም አላቸው ። ሁለተኛ ገብተህ ቀድስ አሉት አይቻለኝም አላቸው ፥ ይህ ሰው ወደ ቀደሙ ግብሩ ተመለሰን ብለዋል ወደ እመቤታችን አመለከተ እድ ብርሀት ቀጠለችለት ገብቶ ሲቀድስ የእጁ ብርሃን እየበዘበዘ የማያሳያቸው ሆነ ወጥተው አባታችን ነገሩ ምንድነው ግለጥልን አሉት ምንጣፏን ግለጡት አላቸው ቢገልጡት ወድቃ አገኟዋት ይህች የኔ እጅ ናት ይህች እመቤታችን የሰጠችኝ ናት ብሏቸዋል ።

ወእመኒ እግርከ ዘየማን ታስሕተከ ምትራ ወግድፋ እምላዕሌከ ።

ቀኝ እግርህ ምክንያተ ስሕተት ብትሆንብህ ቆርጠህ ጣሳት ፤ እስመ ይኄይሰከ ይትጎጐል ፩ዱ እምአባልከ እምዘሎ ሥጋከ ይትወደይ ውስተ እሳተ ገሃነም በዚህ ዓለም ከሕዋላትህ አንዱ ሳይጎድል ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትወርድ፤በዚህ ዓለም ከሕዋሳትህ አንዱ ጐድሎ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ። ይህን ያደረጉ ብዙ ናቸው ከዚያው ግን አባ መርትያኖስ፡በዓቱ ከመንደር አጠገብ ነው ከበረሃ ውሎ ወደማታ ሲመለስ ዘማት ተሰብስበው አይተው ይህ መነኮስ ኃያል ጽኑዕ ነው የሚያስተው የለም አሉ ፤ አንዲቱ እኔ ባስተውስ ባታስችውስ ተባብለው ተወራርደዋል ፤ አሁን በጊዜ የሄድኩ እንደሆነ አይቀበለኝም ብላ ሲመሽ ሒዳ እጅ ጾፋች ፤ ወጥቶ ማነሽ አላት ከሩቅ አገር የመጣሁ የእግዚአብሔር እንግዳ ነኝ የምጠጋበት አጥቸ አውሬ ይጣላኛል ወምበዴ ይቀጠቅጠኛል ብየ ቁሚያለሁ አለችው አዑም በስገባት ጻር ይነሣብኛል አይሆንም ብላት

ነግደ ኮንኩ ወኢተወከፍክሙኒ ያለው ይፈርስብኛል እያለ ያወጣ ያወርድ ጀመረ ። ነግደ ኮንኩ ወኢተወከፍክሙኒ ያለውስ ቢፈርስብኝ ቦሩን አታግሠዋለሁ ብሎ እሳቱን እንድዶላት እሱ አልፍ ብሎ አሎቱን ያዘ እሷም የምትቀባውን ትቀባ የምታጤሰውን ታጤስ ጀመር ። መዓዛው ቢያስቸግረው እግሩን ከእሳቱ ማገደው የእሷን መዓዛ እስኪያጠፋው እስኪለው ጠው ፤ ምትሩ ያለው ለዚህ ይመቻል ፣ እሷም አባቴ አላበጀሁም ብላ ንስሐ ገብታለች አንድም ገልጣ አንተኛ አለችው አንተኛማ ካልሽ ከእሳቱ ላይ አንተኛ አላት ይህማ ይፈጀን የሰም አለችው የዚህን ዓለም እሳት ያልቻልነው የወዲያኛውንማ ዓለም እሳት እንደምን እንችለዋለን አላት አባቴ አላበጀሁም ማረኝ ብላ ንስሐ ገብታለች እሱም አመንዝሯት በእቱን ሊቆላትሂዷል አንድም ዓይን የተባለች ሚስት ናት። ከዓይን የሚሰወር እንደሌለ ከሚስትም የሚሰወር የለምና ፣ ሚስትህ ያልሆነ ሥራ ላሠራህ ብትል ፈቃዷን አፍርስባት ዛሬ በዚህ ዓለም የሚስትህን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትገባ በዚህ ዓለም የሚስትህን ፈቃድ አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፣ እጅ የተባሉ ልጆች ናቸው ወድቆ ይነሡ በእጅ ዜግት ይከብሩ በልጅ እንዲሉ ። ልጆችህ ያልሆነ ሥራ እና ሠራህ ቢሉ ፈቃዳቸውን አፍርስባቸው ፣ በዚህ ዓለም የልጆችህን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትወርድ፤ በዚህ ዓለም የልጆችህን ፈቃድ አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና እግር የተባሉ ቤተሰብእ ናቸው ቤተሰቦችህ ምክንያተ ቤሕተች ሁነው ያልሆነ ሥራ እናሠራህ ቢሉ ፈቃዳቸውን አፍልባቸው ፣ በዚህ ዓለም የእፋቸውን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም እሳት ከምትገባ ፣ በዚህ ዓለም ፈቃዳቸውን አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፤ አንድም አንዳይንህ እንደ እጅህ እንደ እግርህ የምትወደው ወዳጅህ ያልሆነ ሥራ አሠራሃለሁ ቢልህ ፈቃዱን አፍርስበት በዚህ ዓለም የሱን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትገባ ። በዚህ ዓለም የሱን ፈቃድ አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፤ አንድም ምድራውያን ነገሥታት ዓይን በፍላት እጅ እግር በሰለት ፣ እንዲቀጹ ሌዋውያን ካህናት ዓይንን በአንቃዕድዎ እጅን በሰፊሀ ፤ እግርን በቀዊም ፣ ሠርተው ቀጽተው እንዲኖሩ ፤ አንተም ዓይንህን በአንቃዕድዎ እጅህን በሰፊሀ እግርህን በቀዊም ሥራ ቅጻ ።

፴፩ ሰማዕክሙ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ ኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ ይጽሐፍ ላቲ መጽሐፈ ሕዳጋቲሃ ወየሀባ ። ዘዳ ፳፬፡ ፩ ማቴ ፲፱፡፯፡፱ ማር ፲፡፲፪ ሉቃ ፲፮፡፲፰ ፩ ቆሮ ፯፡ ፲ ።

፴፩ ከናንት አስቀድሞ ለነበሩ ሰዎች ሚስቱን የሚፈታ ሰው ሁሉ የምትፈታበትን ነውር የሚናገር ደብዳቤ ጽፎ ሰጥቶ ይፍታት የተባለላቸውን ሰምታችኋል ፣ እንዳለፈው በል ።

፴፪ አንሰኬ እብለክሙ ከመ ኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ ዘእንበለ ትዝሙ በላዕሌሁ ለሊሁ ረሰያ ዘማ

፴፪ እኔ ግን ሳትሰስንበት ሰነፈች ደረቀች ብሎ ሚስቱን የፈታ ሰው ሁሉ ዘማ አሰኛት ብየ እነግራችኋለሁ ።

ወዘሂ አውሰበ ኅድግተ ዘመወ በነውር የተፈታችውን ያገባ በደለ ፣ በምን ያውቀዋል ቢሉ አፁን ዕጨጊ ይፍቱኝ ባለማለቷ ፣ ኋላ እንደምን ትሁን ቢሉ የፍርድ መጽሐፍ በጉኑዓ ብሎ ወስዶታል ። ንስሐ መግባቷን መምህረ ንስሐዋ ጉረቤቶቿ መስክረውላት ታግባ ብሏል ። አንድም ሰማዕክሙ ብለህ መልስ ። አሪትን የሚተው ሰው ሁሉ ወንጌልን ተክቶ ይተው የወንጌልን ሥራ ሳይሠራ ግን አሪትን የተወ ሰው ወንጌልን ኃላፊት ሕግ አደረጋት ። ከተዋትም በኋላ ወደ አሪት ቢመለስ በደለ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል አንድም መልስ ይህን ዓለም የሚተው ሰው ሁሉ መንግሥተ ሰማያትን ተክቶ ይተው ። የምናኔ ሥራ ይሥራ ። ወአንሰ እብለክሙ ፤ የምናኔ ሥራ ሳይሠራ ይህን ዓለም ተውሁ የሚል ሰው ግን መንግሥተ ሰማያትን ኃላፊት ርስት አደረጋት ። ከመነነም በኋላ ወደኋላም ቢመለስ በደለ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል።

፴፫ ወካዕበ ሰማዕክሙ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ ኢትምሐሉ በሐሰት ፣ ወባሕቱ አግብኡ መሐላክሙ ለእግዚአብሔር ። ዘሌዋ ፲፱፡፲፪ ዘፀ ፳፡፯ ዘዳ ፳፫፡፳፩ ያዕ ፭፡፲፪ ፣

፴፫ ለቀደሙ ሰዎች በእውነት እንጂ በሐሰት በስመ እግዚአብሔር እንጂ በስመ ጣዖት ዳኛ ፈርዶባችሁ ባለጋራ አውርዶላችሁ እንጂ ዳኛ ሳይፈርድባችሁ ባለጋራ ሳያወርድላችሁ አትማሉ ያሏቸውን ሰምታችኋል ።

፴፬ ወአንሰ እብለክሙ ኢትምሐሉ ግሙራ ።

፴፬ እኔ ግን ፈጽማችሁ አትማሉ እላችኋለሁ ኢበሰማይ ።
በሰማይም ሁኖ ከሰማይ የመጣ መቅሠፍት አይላተን ሰማይ ተንዶ ይጫነን እያሉ ይምላሉና ፣ እስመ መንበሩ ለእግዚአብሔር ውእቱ ።
የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና ።
ወኢበምድር ።

በምድርም ሁኖ ምድር ይክዳን ምድር ተከፍቶ ይዋጠን እያሉ ይምላሉና ።
እስመ መከየደ እገሪሁ ይእቲ ፣
መመላለሻው ናትና ።

ግዛጸ ሰሎሞን ታውቋል ። ይህስ እዝራ ነሥእን ወኢስተጋብእን ይለዋል ብሎ ተናግሮት ሳይጸፍ የቀረ ነው ። ተናግረውት የቀረውን ማምጣት ለሐዋርያት ልማድ ነው ። ተዓቀቡ በመዋዕለ አፅራር ያለውን በከመ ይቤ ኢዮብ እንዳሉ እንደ ናዝራዊ እንደ ሶምሶን ይባላል ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ በናዝሬት ኖረ ፤ እንድም በኦሪቱ እስመ ናዝራዊ ሐዲስ ውእቱ ለእግዚአብሔር ያለውን እንዲህ ለውጦ አንብበው ፤ ይህንግ የተናገረ መልአክ አይደለም ስለምን ነቢይ አለው ቢሉ ፤ መልአክ ይሰመይ በእንተ ተልእኮቱ ወሐዋርያ ይሰመይ በእንተ ሐዊሮቱ እንዲል ፤ ከዚያ በግብሩ መልአክ እንደ አለው ከዚህም በግብሩ ነቢይ አለው ። ያውስ ቢሆን ይህ የተነገረ ለሶምሶን አይደለምን ቢሉ ፤ ለጊዜው ለሶምሶን ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ ነውና ፤ አነ እከውኖ አባሁ ወውእቱ ይከውነኒ ወልድየ ያለው ለጊዜው ለሰሎሞን ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ እንደ ሆነ ያውስ ቢሆን በምን ይመስለዋልና እንዲህ አለ ቢሉ ፤ ሶምሶን በተናቀች መንሰከ አድግ ጠላቶቹን እንዳጠፋ ጌታም አይሁድ አጋንንት መናፍቃን በናቁት ሞቱ ሞትን አጥፍቷልና ። ሶምሶን በሕይወተ ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው አሕዛብ በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉና ፤ ጌታም በሕይወተ ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው አጋንንት በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉና ። እንድም ከመ ናዝራዊ ይሰመይ ብለህ ናዝሬት ማለት ፍልጠት ክፍለት ማለት ነው ። ልዩ ልዩ ይባል ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ ። ዘተብህለ በነቢይ ስሙ ለልዑል ቅዱስ ቅዱሳን ወይትቀባዕ ቅዱስ ቅዱሳን ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ እንድም ናዝሬት ማለት ኀሥርት ማለት ነው ፤ ይእቲ አሚረ ይሰምያ ለናዝሬት በስመ ኃሣር እንዲል ። ልዩ ኀሡር ይባል ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ እልህን ሡር እንዲል በዓረብ ኀሡር ቢል ፤ እንድም ናዝሬት ማለት እጽቀ ጽጌ ማለት ነው ልዩ እጽቅያዊ ጽጌያዊ ይባል ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ ። እሱ እንዴ ጉንድ ናሁ ምእመናንን እንደ አዕጹቅ እንደ ጽጌያት አድርጎ ያበዛናልና ፤ ያው ግን በነቢይ ቃል ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሤይ ወየዓርግ ጽጌ እምጕንዱ ተብሎ የተነገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው ።

በእንተ ስብከተ ዮሐንስ ።

ምዕራፍ ፫ ፤

፩ ወበውእቱ መዋዕል በጽሐ ዮሐንስ መጥምቅ እንዘ ይሰብክ በገዳመ ይሁዳ ዘዮርዳኖስ ፤

፩ ከመ ናዝራዊ ይሰመይ ወልድየ ብሎ ነበርና ናዝራዊ በተባለበት ወራት ፤ ቦእ ናዝሬት ብሎ ነበርና ናዝሬት በገባበት ወራት ፤ ሃያ አምስቱን ዘመን አንድ ወገን አድርጎ ወበውእቱ መዋዕል አለ በዮሐንስ አርባውን ቀን አንዳንድ ቀን አድርጎ ወእመ ሳኒታ እንዳለ ። እንድም ወተወልደ ብሎ ነበርና ሥጋ በሆነበት ወራት ። እንድም ለዮሐንስ ሠላሳ ሲመላው ለጌታ መንፈቅ ሲቀረው በዚያ ወራት የዮርዳኖስ አውራጃ በምትሆን በይሁዳ ምድረ በዳ ዮሐንስ መጥምቅ ሲያስተምር ደረሰ ፤ በገዳም አለ ቦታው ነውና እንድም በገዳም ዕንጨት ሰባሪ ውኃ ቀጂ አይታጣምና ፤ እንድም በገዳም ጸር ይቀላል ለወጣንያን አብነት ለመሆን በገዳም ጸር ይጸናል ለፍጹማን አብነት ለመሆን ፤ እንድም ገዳም የአይሁድ ልቡና ነው ። በገዳም እፀል ተክል እንደማይገኝ በአይሁድም ልቡና ምግባር ሃይማኖት አይገኝምና እንድም ኢሳይያስ ቃለ ዓዋዲ ዘይሰብክ በገዳም ብሎ የተናገረልኝ እኔ ነኝ ሲል ።

፪ እንዘ ይብል ነስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ፤ ማር ፩ ፡ ፬ ፤ ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፫ ።

፪ መንግሥተ ሰማያት በልጅነት ልጅነት በሃይማኖት ልትሰጥ ቀርባለችና እመኑ እያለ ሲያስተምር ደረሰ ።

፫ እስመ ዝንቱ ውእቱ ዘተብህለ በኢሳይያስ ነቢይ እንዘ ይብል ቃለ ዓዋዲ ዘይሰብክ በገዳም ። ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፫ ። ማር ፡ ፩ ፡ ፫ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

፫ ፤ በገዳም የሚያስተምር ዐዋጅ ነጋሪ ተብሎ በኢሳይያስ ቃል የተነገረለት ይህ ዮሐንስ ነውና ቃለ ዐዋዲ ፤ አዕዋዲ ቃል ይላል ትምህርቱን ከዚያም ከዚያም የሚያደርስ ማለት ነው ቃል ዓዋዲ ይላል ። ይህንንም ቃል ዘይኬልህ በገዳም ብሎ ሊቁ ወስዶታል ።

ወይቤል ጺሑአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ፤
የእግዚአብሔርን መንገድ ጽረጉ ። ወርቱዓ ግበሩ መጸያሕቶ ።

ጽርጊያውን የቀና አድርጉ እያለ ሲያስተምር ደረሰ ሐተታ ፤ ንጉሥ በመጣ ጊዜ ተራራው ከረብታው ተንዶ ጉድጓዳው መልቶ ሥሩ ተነቅሎ ደንጊያው ተለቅሞ ለፈረስ ለሠረገላ እንዲመች ቀና ልድሉ ይቆያልና በዚያ ግሥ ተናገረው ። የእግዚአብሔር ማደሪያ ሰውነታችሁን ከኃጢአት ከጣኦት ንጹሕ አድርጉ ።

፬ ወልብሱ ለዮሐንስ ኮነ እምፀጕረ ገመል ፤ ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ነገሥታት እንጂ ኪያ ሳንቃ ያልብሱኝ ብሎ ነው ትሉኝ እንደሆነ ፤ ይህ ለሥጋውያን ነው ። እሱ ግን መንፈሳዊ ነውና

፬ ይህን አይሻም ፤ ዮሐንስስ የሚለብሰው የግመል ጠጕር ነበር ። ሐተታ የግመል ምን ጠጕር አላትና ቢሉ ከጋማዋ ከጅራቷ ቢፈልጉ አይታጣም

ልብሱን ሲል ወምበዴ ይጣሳዋል ብላ እናቱ ያነን አሥርታ አልብሳው ነበር ፣ አንድም ገመል በቀለኛ ናት አጥብቆ የመታትን እስከ ፯ እስከ ፲ ዓመት አትዘነጋም ባጥብላ ትረግጠዋለች ሥፍራ ሲመቻት ገደል ገፍታ ትጥለዋለች ። እሱም ወይወድይዎሙ ውስተ እቶነ እሳት የምትል ሕገ በቀል ወንጌልን አስተምራለሁ ሲል ። አንድም ገመል ሁለት ግብር አላት ። የሚበላና የማይበላ እንደ ላምና እንደ በሬ ምንዛገ ታወጣለች እንደ ፈረስ እንደ በቅሎ ሰኮናዋ ጽፉቅ ነው ። እስመ ገመል ጽፉቅ ሰኮናሁ ወያመስኩዕ እንዲል ። እሱም ሕገ እሕዛብ ወሕዝብ ወንጌልን አስተምራለሁ ሲል ፣ አንድምገመሉ የሚባል ዕፅ አለ ቆርጠው አድርቀው ከባሕር የጣሉት እንደ ሆነ ጭረት ይወጣዋል ያነን ታትታ አልብሳዋለች ለጊዜው ኑሮው በገዳም ነውና ልብሱን ሲል ወምበዴ እንዳይጣሳው ነው ። ፍጻሜው ግን ለምእመናን አብነት ለመሆን ተርታ ልብስ ለብሳችሁ አልባሌ መስላችሁ ኑሩ ለማለት ።

ወቅናቱ ዘአዲም ውስተ ሐቌሁ ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ነገሥታት እንጂ የወርቅ ዝናር ያስታጥቁኝ ብሎ ነው ትሉኝ እንደሆነ ። ይህ ለሥጋውያን ነው ። እሱ ግን መንፈሳዊ ነውና ይኸን አይሻም ። እሱስ ወገቡን የሚታጠቅበት ዓረብ ነበር ፤ ያ ከደመ ነፍስ የተለየ እንደሆነ ፣ እሱም ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ልዩ ነኝ ሲል ፣ ይኸን አስቀድሞ ከደመ ነፍስ ይለዩታል ከወኃ ይነከሩታል ኋላ ጣጉሩን ይመልጡታል ያስፉታል ቀለም ያገቡታል ፣ ከደመ ነፍስ እንዲለዩት መክር አስተምሮ ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ይለያቸዋል ፣ ከውኃ እንደ መንከር ያጠምቃቸዋል ያስተምራቸዋል እንደ ማልፋት ምግባር ሃይማኖት ያሠራቸዋል ቀለም እንደ ማግባት ጸጋ ክብር ያሰጣቸዋል ዮሐንስ ግን እንዲህ ማድረጉ ፍትወት እንስሳዊት ሠባሕርዩ እያለች በገቢር እንዳላወረዳት ያጠይቃል ።

ወሲሳዩ አንበጣ ወመዓረ ገዳም ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ነገሥታት እንጂ ጣዐ ጋዐዶሮ ሰቅሰቆ ያብሉኝ ብሎ ነው ትሉኝ እንደ ሆነ ይህ ለሥጋውያን ነው ፤ እሱ ግን መንፈሳዊ ነውና ይህን አይሻም ምግቡም አንበጣ የሚባል ቅጠል ደቁሶ ጨው ነስንሶ ነበር ፣ አንድም አንበጣ በልሳነ አቴና ቀምሲስ ይለዋል በኛም ሰበቦት የጋጃ ማ ይባላል ። ወመዓረ ገዳም አለ ። የማንማር ይሏል ፣ አንድም አንበጣ ይላል በቁሙ አንበጣውን ይበላው ነበር ፤ በዐረቡ እልጅራድ ይላል አንበጣ ሲል ፣ ሐተታ ፣ በዘመኑዋ እያሉ እንድታልፍ ለማጠየቅ ኦሪትን አይጠብቋትም ነበር።በ፫ ቀን ግዙሩ የምትለውን ኢያሱ በ፵ ዘመን ገዝሯል ። ሶምሶን ከአፈ አንበሳ መዓር አግኝቶ ተመግቧል ከመንሰከ አድግ ውኃ ጠጥቷል ። ኤልያስም በአፈ ቋዕ ሥጋ እየመጣለት ይበላ ነበር ፣ ዮሐንስም በቁሙ አንበጣውን ይበላው ነበር ። ወመዓረ ገዳም ባለው ወመዓረ ጸደና ይላል ፣ የጣዝማ ማር ፣ ይህንም ሊቁ ጽንበጣ ዘይቢ ልዕልና ስብከቱ ይእቲ ፣ መዓር ዘይቢ ጣዕመ ስብከቱ ይእቲ ብሎ ተርጉሞታል ።

፭ ወየሐውሩ ኀቤሁ ኵሎሙ ሰብአ ይሁዳ ወኢየሩሳሌም ወኵሉ እድያሚሃ ለዮርዳኖስ ።
ማር ፩ ፣ ፭ ።

በኢየሩሳሌም በይሁዳ በዮርዳኖስ አውራጃ ያሉ ሰዎች ሁሉ ከሱ ዘንድ እየሄዱ ፣

፮ ወያጠምቆሙ ለኵሎሙ በፈለገ ዮርዳኖስ እንዘ ይትአመኑ ኃጣውኢሆሙ ።

፮ ኃጢአታቸውን እየነገሩት በዮርዳኖስ ያጠቃቸው ነበር ። እገሌ ተጠመቅ በማየ ንስሐ ከመ ትኩን ረድአ ለክርስቶስ እያለ ፤ ሐተታ ፣ ጥምቀት ከሦስት ወገን ነው ። መዝገበ ውሉድ ፍቁራን የምትባል የጌታ ጥምቀት ፣ ጥምቀት ዮሐንስ ጥምቀተ አይሁድ ፣ ጥምቀተ አይሁድና ጥምቀተ ዮሐንስማ አንድ አይሆንም ሁሉም ልጅነት አያሰጥ ቢሉ አንድ አይደለም ከሰውነታቸው ሰውነቱ እንዲበልጥ ፣ ከጥምቀታቸውም ጥምቀቱ ይበልጣል ። አንድም ፫ ወገን ነው ፩ቱ ምሳሌ ፩ቱ አማናዊ ፣ ምሳሌ አጥመቃ ለምድር በማየ አይሁ ፣ ወለኵሎሙ አበዊነ አጥመቆሙ ሙሴ በደመና ወበባሕር ፣ ወተጠምቃ እገሪሆሙ ለካህናት ያለው ፤ ጥምቀተ ዮሐንስ ፤ ይህ ምሳሌ ነው ። አራቱ አማናዊ መዝገበ ውሉድ ፍቁራን የምትባል የጌታ ጥምቀት እንብዓ ንስሐ፣ ደመ ሰማዕት ባሕረ እሳት ።

፯ ወሶበ ርእየ ብዙኀነ እሕዛበ እምፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን እንዘ ይመጽኡ ውስተ ጥምቀቱ ጽሚተ ። ሉቃ ፫ ፣ ፯ ።

፯ ከጸሐፍት ከፈሪሳውያን ወገን ብዙ ሰዎች ጻድቃን መሰለው ኃጢአታቸውን ሰውረው አልባሌ መስለው ተርታ ልብስ ለብሰው የኦሪትን መፍረሻ የወንጌልን መታነሚ እናያለን ብለው እሱ ወደሚያጠምቅበት ሲመጡ ባየ ጊዜ ፣ ሐተታ ፣ እሥራኤል አይደለም ስለምን እሕዛብ አላቸው ቢሉ ስለብዛታቸው ፣ አንድም በጸያፍ የገባ ግብረ እሕዛብ ይሠራሉና ፣ ባባታቸው በፋሬስ ፈሪሳውያን በሳዶቅ ሰዱቃውያን ተብለዋል ባባትም ስም መጠራት ልማድ ነው ። በዔቦር ዕብራውያን በይሁዳ አይሁድ እንደ ተባሉ ።

ወይቤሎሙ አ ትውልደ አራዊተ ምድር መኑ አመረከሙ ትጕየዩ እመቅሠፍት ወእመንሱት ዘይመጽእ ።

እናንተ የፍኝት እባብ ልጆች በነፍስ በሥጋ ከሚመጣው መከራ ትድኑ ዘንድ ማን ነገራችሁ ። እመ ቅሠፍት ወእመንሱት ወእመዓት ዘይመጽእ ይላል ። በጥሙስ በሐሳዌ መሲሕ በምጽዓት ከሚመጣው መከራ ትድኑ ዘንድ ማን ነገራችሁ ። ሊማሩበት እንዳልመጡ ያውቃ የለምን ቢሉ የማይጠቀም ከጉባኤው አይመጣምና እንድም የሹም ስንፍ ባይለፈልፍ እንዲሉ ፤ ንግር ወኢታርምም ብሎታልና ። አባቶቻቸው ወደው ባወጡት ስም ትውልደ አራዊተ ምድር አላቸው ። ወንድማቸውን የቤፍን ሽጠው በልተው እኩይ አርዌ በልዖ ብለው ነበርና ። ትውልደ አራዊተ ምድር ያላት አርዌ ገሞራዊት ናት አፈ ማኅፀኑዋ ጠባብ ነው ዘሩን ባፏ ትቀበለዋለች አፃሉ ዘሩን ቆርጣ ታስቀረዋለች ። በፅንስ ጊዜ አባት ይሞታል በሚወለዱበትም ጊዜ አፈ ማኅፀኑዋ ጠባብ ነውና ሥጋዋን በልተው ሆዷን ቀደው ይወጣሉ ፤ በዚህ ጊዜ እናት ትሞታለች እኒህም እንዳባት የሚሆኑዋቸውን ነቢያትን እንደ እናት የሚሆኑዋቸው ሐዋርያትን ገድለዋልና ። ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም እንተ ትቀትሎሙ ለነቢያት ወትዌግሮሙ ለሐዋርያት እለ ተፈነው ኀቤየ ብሎ እንዲያመጣው

፰ ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሥርናየ ዘይደልወክሙ ለንስሐ ።

፰ ከእንግዲህስ ወዲህ ለማመን የሚያበቃችሁን ሥራ ሥሩ ።

፱ ወኢይምሰልክሙ ዘታመሥጥሉ በብሂለ ዘትብሉ አብ ብነ አብርሃም ፤ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፴፱ ።

፱ አብርሃምን ያህል አባት ሳለን ትውልደ አራዊተ ምድር ይለናል በማለት ትውልደ አራዊተ ምድር ከመባል የምትድኑ አይምስላችሁ ፤ እንዲሉት ዐውቆ አመጣ እንዲሉትም ዐውቆ ማምጣት ልማድ ነው ። ብጹዓን ብጹዓን እያለ ሲያስተምር ሰምተው ኦሪትን ነቢያትን ሲያባልፋቸው መጥቷል እንዲሉት ዐውቆ ኢይምሰልክሙ ዘመጻእኩ እስዓሮሙ ለኦሪት ወነቢያት ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ እፈጽሞሙ እንዳለ ። ወኢትሁቦ ለጻድቅከ ይርአይ ሙስና ቢላቸው ፤ ይህንማ ዳዊት የተናገረው ለራሱ አይደለም እንዲሉት ዐውቆ ታበውሁ ነሁ እስብእ ንንግርክሙ ክሡተ በእንተ ዳዊት ርእሰ አበው ቀደምት ከመሂ ሞተ ወተቀብረ እንዳለ ከዚህም እንዲህ አለ ።

እብለክሙ ከመ ይክል እግዚአብሔር እምእላንቱ አዕባን አንሥኦ ውሉድ ለአብርሃም ፤ እግዚአብሔር ለአብርሃም ከነዚህ ከአሕዛብ ልጅ ማሥነሣት አቅሞ ውሉድ ይላል መተካት እንዲቻለው ይቻለዋል ብየ እነግራችኋለሁ ፤ አንሥእ ውሉድ አንሥእ ውሉደ ይላል ። እላንቱ አላቸው አሁን ያሉ በመካከል ነውና ኋላ ብሔረ ጌርጌሴን ገባ ብሎ እንዲያመጣቸው ፤ አዕባን አላቸው ደንጊያ ያመልካሉና ፤ አንድም ይቡስ ነው ይቡሳን አእምሮ ናቸውና ፤ ቆሪር ነው ቆሪራን አእምሮ ናቸውና ፤ ክቡድ ነው ክቡዳን አእምሮ ናቸውና ።

፲ እስመ ናሁ ተሠይመ ማሕፄ ውስተ ጕንደ ዕፀው ይኄበር ፤

፲ ምሳር ዓፅቁን ከግንዱ ሊለይ ተቃጥቷልና ። ማለት የናንተን ልጅነት ከአብርሃም አባትነት ሊለይ ሥልጣነ እግዚአብሔር ተቃጥቷልና ኢይምሰልክሙ በብሂለ ዘትብሉ ላለው ፤ ወንጌል ሕገ አሕዛብ ወሕዝብ ዐና ተሠርታለችና ፤ እብለክሙ ከመ እግዚአብሔር ይክል አንሥእ ውሉድ ላለው ፤ መለኮት ከሥጋ ተዋሕዷልና መኑ አመረክሙ ላለው ክፉውን ሕሊና ከበጎ ሕሊና ሊለይ ሥልጣነ ክህነት ተቃጥቷልና ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሠናየ ዘይደልወክሙ ለንስሐ ላለው ፤

ኵሉኬ ዕፅ ዘኢይፈሪ ፍሬ ሠናየ ይገዝምዎ ወውስተ እሳት ይወድይዎ ።

በጎ ፍሬ የማያፈራውን ዕፅ ሁሉ ይቆርጡታል በእሳት ያቃጥሉታል ፤ በኔ ትምህርት አምኖ በጎ ሥራ የማይሠራውን ሰው ሁሉ ነፍሱን ከሥጋው ይለዩታል በገሃነም ሥቃይ ያመጡበታል ።

፲፩ አንሰኬ አጠምቀክሙ በማይ ለንስሐ ፤ ማር ፩ ፡ ፰ ፡ ሉቃ ፫ ፡ ፲፮ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ግብ ሐ ፡ ፩ ፡ ፭ ። በዚህ ያልተያያዘ ቢሉ ቃሉ የተያያዘ ነው ባለጸጎች መጥተው ምንተ ንግበር አሉት ፤ ዘቦ ፪ ልብስ ይሁብ ፩ደ ለዘአልቦቱ ወዘቦ ሲሳይ ከማሁ ይግበር አላቸው ፤ ኃጥአን መጸብሓን መጥተው ምንተ ንግበር አሉት ። አልቦ ፍድፋዴ ዘትገብሩ እምዘተአዘዘክሙ አላቸው አንበሳ ወደቅ የወርቅ ተኩስ የግምጃው መከንጃ የላሙን መንጃ እያሉ የሚወስዱት እላቸውና ፤ የደል ጭፍራ መጥተው ምንተ ንግበር አሉት ፤ ኢትግፍዑ ወኢትሂዱ መነሂ አላ ንበሩ በበሲሳይክሙ አላቸው ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ክርስቶስ እንጂ ቢሆን ነው ብለዋል እኔስ ለጼጅ ቢረሉን

፲፩ ስልብሱ ግን እንዲያጽቡለት ስሉ ጥምቀት በሚያበቃ ጥምቀት አጠምቃችኋለሁ ስሉ ተእምምኖ ጣውእ በሚያበቃ ተእምኖ ኀጣውእ አስተምራችኋለሁ እንጂ ክርስቶስ አይደለሁም ።

ወዘይመጽእ እምድኅሬየ ውእቱ ይጸንዕ እምኔየ ። ከኔ በኋላ የሚመጣው እሱ ከኔ አስቀድሞ የነበረው ነው አለ ። የባሕርይ አምላክ ነው ።

ዘኢይደልወኒ እጹር ዓሣዕኖ ። ጫማውን ልይዝ የማይገባኝ ። ሐተታ ፤ የንጉሥን የንግሥትን ጫማ ትቢቃለህ ያላሉት ሰው አይዝምና ።

አንድም ባሕርዩን ለመረምር ከማይቻለኝ ፤ አንድም ፣ እሱ ከሚያደርገው ከታምራቱ ከትሩፋቱ አንዱን ሳደርግ ከማይቻለኝ ፣ አንድም አግዐነ መርገምን ከምእመናን ለአንዱ አርቅለት ዘንድ ከማይቻለኝ ከኔ አስቀድሞ የነበረ ነው ።

ውእቱስ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወበእሳት ፤ እሱ ግን በጀ ብትሉ በመንፈስ ቅዱስ በጀ ባትሉ በገሃነመ እሳት ያጠምቃችኋል ፤ ዋነምቱ ምድር ይእቲ እንተ ኢትመልዕ ማየ እንዲል ፤ አንድም በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያጠምቃችኋል ። ሐተታ ፣ መንፈስ ቅዱስን እሳት አለው ፣ እሳት ምሉእ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ምሉእ ነውና ፣ እሳት በምልአት ሳለቡሳድ ከልመቱ አይገለጽም ። መንፈስ ቅዱስም ቋንቋ ሲያናግር ምሥጢር ሲያስተረጉም እንጅ ሕድሮ ሳለ አይታወቅምና ፣ እሳት ከቡላዱ ሲወጣ በመጠን ነው ኋላ በዕንጨት እያቀጣጠሉ ያስፋታል መንፈስ ቅዱስም በጥምቀት ሲሰጥ በመጠን ነው። ኋላ በሥራ ያስፋታልና እሳት ጣዕምን መዓዛን ያመጻል ፣ መንፈስ ቅዱስም ጣዕመ ጸጋን መዓዛ ጸጋን ያመጣልና፣እሳት በመጠን ቢሞቁት ሕይወት ይሆናል ። ከመጠን ወጥቶ የሞቁት እንደሆነ ግን ያቃጥላል ። መንፈስ ቅዱስም በሚገባ በተጸፈው የመረመሩት እንደሆነ ሕይወት ይሆናል ፤ በማይገባ ከተጻፈው ወጥቶ የመረመሩት እንደሆነ ግን ይቀስፋልና እሳት በሳኢ ሰዓግዐያን ለእለ ይከህዱ ስሞ ወእሳት ማሕየዊ ለርቱዓነ ልብ ለእለ ይገብሩ ፈቃዶ እንዲል ፤ እሳት ያቀረቡለትን ሁሉ ያቃጥላል መንፈስ ቅዱስም ሕዝብ አሕዛብ የጸለዩትን ጸሎት ያቀረቡትን መሥዋዕት ይቀበላልና ፣ እሳት ወኃ ገደል ካልከለከለው ሁሉን ሳጥፋ ቢል ይቻለዋል ። መንፈስ ቅዱስም ቸርነቱ ካልከለከለው ሁሉን ሳጥፋ ቢል ይቻለዋልና እሳት ዱር ይገልጻል መንፈስ ቅዱስም ምሥጢር ይገልጻልና እሳት የበላው መሬት ለእህል ለተከል ይመቻል ፣ መንፈስ ቅዱስም ያደረበት ሰውነት ለገድል ለትሩፋት ይመቻልና እሳት ከዛገላቸው ሳይሳተፍ ሰባቱን መዓድናት ያጸራቸዋል መንፈስ ቅዱስም ከግብራቸው ሳይሳተፍ ሁሉን ያነጻልና ይእቲ ቃነጽሕ ወኢትረክሕ እንዲል ፤ እሳት ካንዱ ፋና እምሳ ስልሳ ፋና ቢያበሩለት ተከፍሎ የለበትም ፤ መንፈስ ቅዱስም ተከፍሎ ሳይኖርበት እስከ ምጽአት ድረስ ሲሰጥ ይኖራልና ይእቲ ትሁብ ወኢትቀብል እንዲል በእሳት ቀድሞ ሰብአ ሰዶም ሰብአ ገሞራን ከእሥራኤል አንዱን ኀብር አጥፍቶበታል ለመዓት እንጅ ለምሕረት አልተፈጠረም እንዳይሉ ለምሕረትም እንደ ተፈጠረ ለማጠየቅ ። አንድም ሸክላ ሠሪ ሠርታ ለትጨርስ ነቅ ያገኘችበት እንደሆነ እንደ ገና መልሳ ከስክሳ በውኃ ለውሳ በእሳት ታድሰዋለች ። ተሐድሶም በመንፈስ ቅዱስ ነውና ፤ ዛቲ እሳት እንተ ኮነ ይትገዐፉ አዳም እንበለ ይትጓደ ትእዛዘ እግዚአብሔር ፈጣሪሁ አመ ነበረ ውስተ ገነት ወሰዐ በልዓ እምዕፀ ዕልወት ተዓርቀ ወኢረከበ እስከነ መጽአ ሊዳም ዳግማዊ ወአል/ሁ እኑመ እግይ ወኢመንፈስ እንዲል

፲፪ ዘመሥኤ ውስተ እዴሁ ዘቦቱ ያነጽሕ ዓውደ እክሉ ።

፲፪ ፍሬውን ከገለባ የሚለይበት መንሽ በጁ ተይዞ ያለ ።

ወያስተጋብእ ሥርናዮ ውስተ መዛግብቲሁ ። ፍሬውን ከገለባው ለይቶ በሬቅ በጎታ በጎተራ የሚሰበስብበት ወኃሠርስ ያውዒ በእሳት ዘኢይጠፍዕ። ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት የሚያቃጥል እሱ ያጠምቀክሙ በል ወደ ወርቅ ሂዶ ዘኢይጠፍዕ አለ ፤ አንድም ዘመሥኤ ብለህ መልስ ፣ ጣቱ ሦስት ነው ቢሉ የሦስትነት መያዣው ያንድነት ሁለት ነው ቢሉ ንዑና ሐሩ የሚልበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን ።

ዘቦቱ ያነጽሕ ዓውደ እክሉ ዘውእቱ ፍጥረት ሰብእ ብሎ ወስዶታል ሊቁ ፣ ጻድቃንን ከኃጥአን የሚለይበት ።

ወያስተጋብእ ሥርናዮ ውስተ መዛግብቲሁ ፣ ጻድቃንን ከኃጥአን ለይቶ በመንግሥተ ሰማያት የሚያኖርበት ፣ መዛግብት ብሎ አበዛ በብዙ ወገን ትወረሳለችና ፣ እሲመ ውስተ ቤተ አቡየ ብዙኅ ማኅደር ወምዕራፍ ቦቱ እንዲል ።

ወኃሠርስ ያውዒ በእሳት ዘኢይጠፍዕ ፣ ኃጥአንን ከጻድቃን ለይቶ በገሃነም ሥቃይ የሚያመጣበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን ፣ አንድም ከፋውን ሕሊና ከበጎው ሕሊና የሚለይበት ሥልጣን ክህነት ገንዘቡ የሚሆን ፣ ወሥርናዮስ በጎውን ሕሊና ከከፋ ሕሊና ለይቶ በመንፈስ ቅዱስ የሚያስጠብቅበት እሱ ፣ መዛግብት ብሎ አበዛ ስለ ሀብቱ ብዛት ወኃሠርስ ፣ ከፋውን ሕሊና ከበጎ ሕሊና ለይቶ በቀኖና የሚያጠፋበት ሥልጣነ ክህነት ገንዘቡ የሚሆን እሱ በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያጠምቃችኋል

በእንተ ጥምቀተ እግዚእ ኢየሱስ

፲፫ ወእሚሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ እምገሊላ ውስተ ዮርዳኖስ ከመ ይጠመቅ እምዮሐንስ

፲፫ ማር ፩ ፣ ፱ ፡ ለጌታ ሠላሳ ሲመላው ለዮሐንስ መንፈቅ ሲተርፈው ያን ጊዜ ጌታ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ። አንድም ሰው ሰብሰቦ በማያጠምቅበት ጊዜ መጣ አብ በደመና ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክር

መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመጥ አንድነት ሦስትነት ይታወቃልና ፤ ያን ጊዜ ጌታ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ አለ ። ሐተታ ምነው ባሪያ ወደ ጌታው ይሄዳል እንጅ ጌታ ወደ ባሪያ ይሄዳልን ፤ ባሪያ በጌታው እጅ ይጠመቃል እንጅ ጌታ በባሪያው እጅ ይጠመቃልን ቢሉ ጌታ መምጣቱ ለትሕትና ነው እንጅ ልልዕልና አይደለምና ፤ አንድም ለአብነትነት ጌታ ዮሐንስን መጥተህ አጥምቀኝ ብሎት ቢሆን ዛሬ ነገሥታት መኳንንት መጥታችሁ አጥምቁን ባሉ ነበርና ፤ ሄዳችሁ ተጠመቁ ለማለት አብነት ስለሆነ ፤ ጥምቀቱን በዮርዳኖስ ያደረገው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ፤ ትንቢት ባሕርኒ ርእየት ወጎየት ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅሬሁ ርእዩከ ማያት እግዚኦ ርእዩከ ማያት ወፈርሁ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አንድ ነው ዝቅ ብሎ በደሴት ይከፈላል ከታች ወርዶ ይገናኛል ። ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አንድ እንደሆነ የሰው ሁሉ ነቁ አንድ አዳም ነው ። ዝቅ ብሎ በደሴት እንዲከፈል እስራኤል በግዝረት አሕዛብ በቍልፈት ተለያይተዋል ። ከታች ወርዶ በወደብ እንዲገናኝ ሕዝብና አሕዛብ በክርስቶስ በጥምቀት አንድ ሁነዋልና ፤ አንድም አብርሃም ላምስቱ ነገሥተ ሰዶም ረድቶ አራቱን ነገሥተ ኮሎዶጎሞርን ድል ነሥቶ ሲመለስ ዶስ ቢለው በመዋዕልየኑ ትሬኒ ቃለከ መሚሑ ታርእየኒሁ ኪያሃ ዕለተ አው አልቦ አለ ፤ እሱንስ አታየውም ምሳሌውን ታያለህና ሑር ዕድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ አለው ፤ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ቢሄድ መልከ ጼዴቅ ኅብስተ በረከት ጽዋዓ አኰቴት ይዞ ተቀብሎታል አብርሃም የምእመናን ዮርዳኖስ የጥምቀት መልከ ጼዴቅ የቀሳውስት ኅብስተ በረከት ጽዋዓ አኰቴት የሥጋው የደሙ አንድም ኢዮብ ከዚህ ተጠምቆ ከደዌው ድኅኖዋል ፤ ኢዮብ የአዳም ከነሕፃናቱ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ፤ አንድም እሥራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል ፤ ምእመናንም እምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ገብተዋልና ፤ ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ገነት አርጓል ምእመናንም እምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ለመግባታቸው ። አንድም የኤልሳዕ ደቀ መዛሙርት ጸበበነ ማኅደር ንዑ ንግዝም ዕፀ ወንሕንጽ ካልዓ ማኅደረ ብለው ሄዱ ፤ እሱም መምህረ ትሕትና ነውና አብሯቸው ሄደ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ሲቆርጥ ምሳሩ ከዛቢያው ወልቆ ከባሕር ገባበት ፤ ዘኒ ኅዑይ እግዚእየ ፤ ጌታዬ ጥንቱን የተዋሰ ያውም ጠፋ ተጨርሶ አለው የገባበትን አሳየኝ አለው አሳየው ቅርፍት ዕፅ ቀርፎ አመሳቅሎ ቢመታው መዝቀጥ የማይቻለው ቅርፍቱ ዕፅ ዘቅጦ መዝቀጥ የሚገባውን ብረት ይዞት ወጥቷል።እንደዚህም ሁሉ ሞት የማይገባው መለኮት ሙቶ ሞት የሚገባው አዳምን ለማዳኑ ምሳሌ ፤ ጥምቀቱንም ሽቶ አላደረገውም ። አኮ ፈቂዶ ለተጠምቆ አላ ከመ የሀበነ ሱታፌ ንጽሕ እንዲል በመጠመቁም ጸጋ ያገኘበት አይደለም ። አኮ ዘረከበ ጸጋ በተጠምቆቱ አላ ከመ ያብርህ መካናተ ወያነጽል ማያተ ለእለ ሀለዎሙ ይጠመቁ ውስቴታ እንዲል ፤ ዮርዳኖስን ብርሀት ማሕፀን ለማድረግ ለጥምቀት ኃይል ለመስጠት ነው እንጂ አንድም ዮርዳኖስ በበጋ የማይጎድል በክረምት የማይተርፍ ማእከላዊ ውኃ ነው የጌታም ጥምቀቱ እኛም ከመጥቀም በላይ እሱን ከመጥቀም በታች ነውና ፤ ዳግመኛ በባሕረ ጥብርያዶስ ላይ የሚሄድ ውኃ ነው ዐባይ በጣና ላይ እንዲሄድ የጌታም ጥምቀት ከኛ ጥምቀት በላይ ነውና ፤ አንድም ብዙ ንዑሳን አንቅዕት ይገቡበታል እሱ ያበረታቸዋል እንጂ እነሱ አያበረቱትም ፤ የጌታም ጥምቀት ለኛ ጥምቀት ኃይል ጽንዕ ይሆናል እንጂ የኛ ጥምቀት ለጌታ ጥምቀት ኃይል ጽንዕ አይሆንምና ። አንድም ንዕማን ከዚህ ተጠምቆ ከደዌው ተፈውሷል ንዕማን የአዳም ከነሕፃናቱ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ፤ ኢዮብን ዕማን ጌታ የተጠመቁበት ወደቡ አንድ ነው ። ትንቢቱን ዐውቆ አናግሯል ምሳሌውንም እንጂ ፀውቆ አስመሰሏል ። ምሥጢሩ እንደምነው ቢሉ ዲያብሎስ የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ በአዳምና በሔዋን ሥቃይ አጸናባቸው ስመ ግብርናታችሁን ጽፋችሁ ብትሰጡኝ ባቀልልሁላችሁ ነበር አላቸው ። አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ ብለው ጽፈው ሰጡት መጽሐፉ የለም ይሁንብን ማስታቸውን መናገር ነው እንጂ እሱ በሁለት ዕብነ ሩካም ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ አንዱን በሲኦል ጥሎታል፤ በዮርዳኖስ የጣለውን ሲጠመቅ እንደ ሰውነቱ ተረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶላቸዋል ። በሲኦል የጣለውን በዕለተ ዓርብ በእካለ ነፍስ ወርዶ ነፍሳትን ሲያወጣ አጥፍቶላቸው ወጥቷል ።

፲፬ ወዮሐንስሰ ዓበዮ እንዘ ይብል አንሰ እፈቅድ እምኀቤከ እጠመቅ ።

፲፬ ዮሐንስ ግን ባሪያ በጌታው እጅ ይጠመቃል እንጂ ጌታ በባሪያው እጅ ይጠመቃልን ብሎ አይሆንም አለው ።

ወአንተኑ ትመጽእ ኀቤየ ፤

ባሪያ ወደ ጌታው ይሄዳል እንጂ ጌታ ወደ ባሪያው ይሄዳልን አለው ፤ እናቱ ምንትኑ አነ ከመ ትምጽእ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ ብላ ነበርና ። ከዚያ አያይዞ እንዲህ አለ ።

፲፭ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ኅድግ ምዕረሰ ።

፲፭ ጌታ መለሰ አንድ ጊዜስ ተው አለው ። ሐተታ ፡ አንድ ጊዜ ቢጠመቅ ሁለተኛ ፡ በፈቃድ ቢጠመቅ በግድ ፡ በሰውነቱ ቢጠመቅ ባምላክነቱ መጠመቅ የለበትምና ።

እስመ ከመዝ ተድላ ውእቱ ለነ ይህ ለኛ ተድላችን ነውና ፤ ሐተታ ፡ ራሱን ከዮሐንስ አግብቶ አንተም መጥምቀ መለኮት ተብለህ ክብርህ ይነገራልና እኔም በባሪያው እጅ ተጠመቀ ተብሎ ትሕትናየ ይነገራልና ወይደልወነ ከመ ንፈጽም ኵሎ ጽድቀ። ትንቢተ ነቢያትን ልንፈጽም ይገባናልና ዮሐንስ እንዲያጠምቅ ጌታ እንዲጠመቅ ትንቢት ተነግሯልና አንድም እስመ ከመዝ ተድላ ለነ ። ራሱን ከምእመናን አግብቶ ይህ ለኛ ተድላችን ነውና ፤ እናንተም ብትጠመቁ ይወርድላችኋል ለማለት ፡ ወይደልወነ ከመ ንፈጽም ኵሎ ጽድቀ ። ጽድቀ ተሰብእን ልንፈጽም ይገባናልና ፡ አንድም ራሱን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ አድርጎ ይህ ለኛ ተድላችን ነውና አለ ። አብ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመጥ አንድነት ሦስትነት ይገለጻልና ። ወይደልወነ ከመ ንፈጽም ኵሎ ጽድቀ ፡ በማኅፀን የጀመርነውን ቸርነት ልንፈጽም ይገባናልና ። ወእምዝ ኀደጎ ።

ከዚህ በኋላ ተወው ። ሐተታ ፡ እንዲያው አይተወውም ስመ አብ ብከ ወስመ ወልድ ለሊከ ወስመ መንፈስ ቅዱስ ሀልው ውስቴትከ ባዕደ አጠምቅ በስምከ ወበስመ መኑ አጠምቅ ኪያከ አለው ወልዱ ለቡሩክ ከማቴ ብርሃን ተማሃለነ ፡ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ብለህ አጥምቀኝ አለው ። ከዚህ በኋላ ተያይዘው ወደ ባሕር ወርደዋል ።

፲፮ ወተጠሚቆ እግዚእ ኢየሱስ ሶቤሃ ወፅአ እማይ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡

፲፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ከውኃው ወጣ ሐተታ ፡ ጥምቀቱን በውኃ ያደረገው በሌላ ያላደረገው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ፡ ትንቢት ወእነዝኃክሙ በማይ ንጹሕ ወትነጽሑ እምርኩስክሙ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም ለታውፅአ ባሕር ኵሎ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈስ ሕይወት ባለ ጊዜ በልብ የሚሳቡ በእግር የሚያሽከረክሩ በክንፍ የሚበሩ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሁነው የሚኖሩ ፍጥረታት ተገኝተዋል ፡ በረው በረው የሄዱ አሉ ከዚያውም የቀሩ አሉ ። በረው የሄዱ የኢጥሙቃን ከዚያው የቀሩ የጥሙቃን ምሳሌ ፡ ይህስ እንዳይሆን ወባረኮሙ ለክልኤሆሙ በአሑቲ ቡረከት ይላል ብሎ በልብ የሚሳቡ የሰብአ ዓለም በእግር የሚያሽከረክሩ ከትሩፋት ወደ ትሩፋት የሚሉ የባሕታውያን ፡ በክንፍ የሚበሩ ተመስጦ ያላቸው የሰማዕታት ምሳሌ ትንቢቱን ዐውቆ አናግሯል ፡ ምሳሌውንም እንጂ ባወቀ አስመስሏል ፍጻሜው እንደምነው ቢሉ ውኃ በዞፋን ካለ ንጉሥ ባደባባይ እስካለ ጽኑስ ለሁሉ ርኩብ ነው ጥምቀት መሠራቱ ለሁሉ ነውና ፡ ውኃ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይፈሳል ። ጥምቀትም ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደረጋልና ። ውኀ ያነጻል ጥምቀትም ያነጻልና ፡ ውኀ ለወሰደው ፍለጋ የለውም በጥምቀትም የተሰረየ ኃጢአት በፍዳ አይመረመርምና ፡ ውኀ መልክ ያሳያል መልክ ያለመልማል ፡ ጥምቀትም መልክአ ነፍስ ያሳያልና መልክአ ነፍስ ያለመልማልና ፡ በውሀ የታጠበ ልብስ ኃይል ጽንዕ ግዘፍ እየነሣ ይሄዳል ምእመናንም ተጠምቀው ገድል ትሩፋት እያከሉ ይሄዳሉና ፡ አንድም ሥጋዊ ተፍኀር የነርብቃ የነሲፓራ በውኃ ምክንያት ሁኖዋል መንፈሳዊ ተፍኀርንም በውኃ ለማድረግ ፡ አንድም ሸክላ ሠሪ ሠርታ ስትጨርስ የነቃባት እንደሆነ እንደገና ከስክሳ በውኃ ለውሳ ታድሰዋለች ። ተሐድሶም በጥምቀት ነውና ፡ አንድም በውኃ ቀድሞ ሰብአ ትካትን ኋላ ግብጻውያንን ካጠፋበት በኋላ ለመዓት እንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም ብለውታል ፡ ለምሕረትም እንደተፈጠረ ለማጠየቅ ። ሐተታ የወዲያኛው ቀስቱን እያጋለ መርዝ እየቀባ እያተባ ይመጣል ። የወዲህኛውም እግዚአብሔር ጥበቡን ገልጾለት ጀባውን ከውኃ ነክሮ ለጋሻው አልብሶ ይሄዳል መርዙን ጀባው ይጠርግለታል ፡ ግለቱን ውኃው ያቀዘቅዝለታል ስለቱን ጋሻው ይመልስለታል እንደዚህ ሁሉ ምእመናንም በጥምቀት ባገኙት ኃይል ድል ይነሳሉና ።

ወናሁ ተርኅወ ሎቱ ሰማይ ፡ ሰማይ ተከፈተለት ። ሐተታ ፡ በሰማይ መከፈት መዘጋት የለበትም ደጅ በተከፈተ ጊዜ የውስጡ እንዲታይ ያልተገለጸ ምስጢር ተገለጸለት ሲል ነው ። ወርእየ መንፈሰ እግዚአብሔር እንዘ ይወርድ ከመ ርግብ ወነበረ ላዕሌሁ። መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ ጥበት አየ ። ሐተታ ፡ መንፈስ ቅዱስን ርግብ አለው ርግብ ኃዳጊተ በቀል ናት ። መንፈስ ቅዱስም ኃዳጌ በቀል ነውና አንድም ርግብ በኖኅ ጊዜ ሐጸ ማየ አይኅ ንትገ ማየ አይኅ ስትል ቈጽለ ዕፀ ዘይት ይዛ ተገኝታለች ፡ መንፈስ ቅዱስም ተስፋ መስቀልን ያበሥራልና ፤ አንድም ርግብ ክንፏን ቢመቷት ዕንቁላሏን ቢሰብሩባት ቤቷን ካፈረሱባት አትሄድም ። መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት ቢሠሩ ፈጽመው ካልካዱት አይለይምና ፤ ታሪክ ፡ አንድ ባሕታዊ እንዳየው ወሉታ ካህን ግልፎን አጊጣ አይቶ

በሐጸ ዝሙት ተንደፈ ። ላማባሽ አላት ላባቴ ንጉረው እምቢ አይልህም አለችው ሂዶ ነገረው ። ፈጣሪዩን ልጠይቅ ብሎ ከጣዖቱ ዘንድ ገብቶ ልስጠው አልስጠው ብሎ ጠየቀው ። ቆቡን ይቅደድ ፈጣሪውን ይካድ ይኸን ካላደረገ አትስጠው አለው ሂዶ ነገረው። ቆቡን ቀደደ ፈጣሪውን ካደ ። በዚህ ጊዜ አድሮበት የነበረ መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ አምሳል ተለይቶት ሲሄድ አይቷል ። ያልኸኝን አደረግሁ ስጠኝ አለው ሁለተኛ ልጠይቅ ብሎ ገብቶ ቢጠይቀው ፥ ቆቡ ፈጣሪውም ፈጽሞ አልራቀውም ባጠገቡ ባጠገቡ ቆጠብቀዋልና አትስጠው አለው ። አይሆንም አለው ፥ ለዚህን ብዬ ፈጣሪዬን ካድሁ ቆቡን ቀደድሁ ብሎ ንስሐ ቢገባ ተመልሶ በርግብ አምሳል ሲያድርበት አይቷል ። ጥምቀቱን በመዓልት ያላደረገው በሌሊት ያደረገው ስለምን ቢሉ ፥ በመዓልት አድርጎት ቢሆን መንፈስ ቅዱስን በቁመ ርግብ ነው ብለው በተጠራጠሩ ነበርና አሁንስ በቁመ ርግብ አለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ በምን ይታወቃል ቢሉ ፥ ጌታ የተጠመቀ ከሌሊቱ ባሥረኛው ሰዓት ነው በዚያን ጊዜ ተሐዋስያን ከየቦታቸው አይናወጡምና ፥ በቁመ ርግብ አለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል፤ መንፈስ ቅዱስም መውረዱ ከውኃው ከወጣ ከዮሐንስ ከተለየ ነው ። ከውኃው ሳለ ወርዶ ቢሆን ለቀድሶተ ማያት የወረደ ነው ባሉ ነበረና ከዮሐንስ ጋራም ሳለ ቢሆን ስለ ክብረ ዮሐንስ የወረደ ነው ባሉ ነበርና ፥ ረቦ ወርዷል ያሉ እንደ ሆነ አብ ምሉእ ነው አንተም ምሉእ ነህ እኔም ምሉእ ነኝ ሲል ፥ አሰይፎ ወርዷል ያሉ እንደሆነ የብሉይ መዋዕል የአብ ሕይወት ነኝ የሐዲስ መዋዕል ያንተም ሕይወት ነኝ እኔም ብሉየ መዋዕል ሕይወት ነኝ ሲል ወርዶ ራሱን ቆንጠጥ አድርጎ ይዞታል አብ እጋዜ ዓለም ነው አንተም እጋዜ ዓለም ነህ እኔም እጋዜ ዓለም ነኝ ሲል ፤ መውረዱ ግን የማኅፀኑን ለመግለጽ ነው ። እንድም ለአብነት እናንተም ብትጠመቁ እንዲህ ይወርድላችኋል ለማለት ወናሁ መጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቀርኩ ዘቦቱ ሠመርኩ ። ሉቃ ፱ ፴፭ ፤ ፪ ጴጥ ፩ ፲፯።

፲፯ ለተዋሕዶ የመረጥሁት ብሎ ህልው ሁኜ ልመለክበት የወደድሁት ልጄ ይህ ነው የሚል ቃል ከወደ ሰማይ ተሰማ ሐተታ ፥ በዚሁ አድሮ ያለው ልጄ ነው አላለም ፩ አካል ፩ ባሕርይ አድርጎ ይህ ልጄ ነው አለ እንጂ ፥ ኢይቤ ዘላዕለ ዝንቱ ወልድየ አላ ይቤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ እንዲል። ወልድየም ማለቱ እንደ አምላክነቱ ነው እንጂ እንደ ሰውነቱ አይደለም ። ኢይቤ ዝንቱ ወልድየ ዘከመ ትስብእቱ አላ ይቤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘከመ መለኮቱ እንዲል ።

በእንተ ተመክሮተ ዘኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወእምዝ ወሰዶ መንፈስ ገዳመ ለእግዚእ ኢየሱስ ። ማር ፩ ፥ ፲፪ ሉቃ ፬ ፩ ፥ ከተጠመቀ በኋላ ፈቃዱ አነሣስቶ ወደ ገዳም ወሰደው ። ወሶበ ትሰምዕ እንዘ ይብለከ መንፈስ ወሰዶ ገዳመ ኢታሐሊ ከመ ፍጡር ውእቱ ፤ አላ መንፈስሰ ሥምረቱ ይእቲ እንዲል ፥ አንድም መንፈስ ቅዱስ የሚል አብነት ይገኛል ሰማዕታትን አነሣሥቶ ወደ ደም ጻድቃንን አነሣስቶ ወደ ገዳም እንዲወስድ ወሰደው ማለት አይደለም ፈቃዳቸው አንድ መሆኑን መናገር ነው ። ተጠምቆም አልዋለም አላደረም ዕለቱን ገዳም ሄዷል ። እናንተም ተጠምቃችሁ አትዋሉ አትደሩ ዕለቱን ገዳም ሂዱ ለማለት አብነት ለመሆን ወደ ገዳም ሄደ አለ ። አዳም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በገነት ድል ተነሥቶ ነበርና ፥ እሱም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በገዳም ፫ቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ለመንሳት ። አንድም በገዳም ጾር ይቀላል ለወጣንያን አብነት ለመሆን አንድም በገዳም ጾር ይጸናል ለፍጹማን አብነት ለመሆን ። ከመ ይትመከር እምዲያብሎስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ፥ እፈተናለሁስ ብሎ ሄዶ ቢሆን ዕዳ በሆነበት ነበር ፥ ከሄደ ዘንድ ጾሩን እየቀለመ ይሰብርበታል እንጂ ።

ይህንም ጾር እማርበታለሁ ብሎ አላደረገውም ንግእ ፩ መዓዱ እምአፍአ ከመ ትኩን ፍቱን ወስቡከ እንዲል መከራውንም ሽቶ አላመጣውም እኮ ፈቂዶ መከራሁ ለጸላኢ አላ ከመ ያብጥል ኃይሎ ለዘያሜክሮ በኃይሉ ለቃሉ ዘኮነ ፩ደ ምስለ ሥጋ እንዲል ። መከራውንም እንዳሣሥቶ አላመጣውም ኢሖከ እግዚእነ እሎንቱ ሕማማተ ከመ ይባልኦ ዲቤሁ አላ ፀሁከቶሙ ማአኑ እንዲል ፥ መዋጋቱም በሰውነቱ ነው ፥ ኢሠርዓ እግዚእ ቀትለ በመለኮቱ አላ በሥጋው ዘይትቄፅፍ ሕማማተ እንዲል ። ድል መንሳቱም በሰውነቱ ነው እንጂ በአምላክነቱ አይደለም። ወኢሞአ በኃይሉ መዋዒት እንዲል ፥ በአምላክነቱስ ድል ቢነሳው ባልተደነቀም ነበር ፥ ሶበሰ ሞአ እግዚእነ በኃይሉ መዋኢት እምአኪነ መንክረ ወእም አኮንኬ ትሩፋት ዘዉስቴቱ ዘኢሰብእ ሕቅወ ኢውድሰት አኮ መንክር እመ ሞአ ኃያል ሰደኩም እንዲል ።

፪ ወጾመ ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ

፪ ፵ መዓልት ፵ ሌሊት ጾመ ። ሠራዔ ሕግ ነውና ጾምን መጀመሪያ ሕግ አደረገ ። እንድም ሥራውን በጾም ጀመረ ። ሐተታ ፥ መብል ለኃጣውእ መሠረት እንደ ሆነ ፥ ጾምም ለምግባር ለትሩፋት መሠረት ናትና ፥ እማ ለጸሎት ወእኀት ለአር

ምሞ ወነቅዓ ለአንብዕ ወጥንተ ዡሉ ገድል ሠናይት እንዲል ። ፵መዓልት ፵ ሌሊት መሆኑ ስለምን ቢሉ ቀድሞ አባቶቹ ነቢያት ፵ ፵ ጹመዋል ከዚያ ቢያተርፍ አተረፈ ቢያጕድል አጕደለ ብለው አይሁድ ደጊቱን ሕገ ወንጌልን ከመቀበል በተከለከሉ ነበርና ፤ ሙሴ በ፵ ዘመኑ ለዕብራዊ ረድቶ ግብጻዊን ገድሎ በኖጻ ቀብሮታል ። ሙሴ የወልደ እግዚአዚአብሔር ዕብራዊ የአዳም ግብጻዊ የዲያብሎስ ኖጻ የመስቀል ። አንድም የ፫ቱ አርእስተ ኃጣውእ ምሳሌ ፤ ሙሴ ፵ ጾም ሕገ ኦሪትን ሠርቷል እሱም ፵ ጾሞ ሕገ ወንጌልን የሚሠራ ነውና ሙሴ ፵ ዘመን በምድያም ኑሮ እሥራኤልን ከግብጽ አውጥቷቸዋል ። እሱም ፵ ጾሞ

ነፍሳትን የሚያወጣ ነውና ፤ አንድም የእሥራኤል ጉበኞች በ፵ ቀን ተመልሰዋል ። እሱም የመንግሥተ ሰማይ ጉበኛ ነውና እሥራኤል በገዳም ፵ ዘመን ኑረው ምድረ ርስት ገብተዋል ። እናንተም ፵ ብትጾሙ ገነት መንግሥተ ሰማያት ትገባላችሁ ለማለት ። ኤልያስ ፵ ጾሞ ገነት ገብቷል ። እናንተም ፵ ብትጾሙ ገነት መንግሥተ ሰማያት ትገባላችሁ ለማለት ሕዝቅኤል በፀጋማይ ጐኑ ፵ ቀን ተኝቶ ሰድስት መቶ ሙታን አስነሥቷል ። እናንተም ፵ብትጾሙ ትንሣኤ ዘለክብር ትነሣላችሁ ለማለት ፤ ዕዝራ ፵ ቀን ከምግቡ ተከልክሎ መጻሕፍትን አጽፏል ። እንስ በውእቶን መዋዕል ኢበላዕኩ እክለ ወኢሰተይኩ ማየ ። እሙንቱሰ መዓልተ ይጽሕፉ ወሠርከ ይደረሩ እንዲል እነዚያ ቀን ሲጽፉ እየዋሉ ማታ ይመገባሉ ። እሱ ግን ቀን ሲያጽፈው የሚውለውን ሌሊት ሲያስበው ያድር ነበር ። እናንተም ፵ ብትጾሙ ምሥጢር ይገለጥላችኋል ለማለት ፤ እነብ አካሉ የደገደገበት እንደሆነ ፵ ቀን ከምግብ ተከልክሎ ይበነብታል ። በስቁረተ ዕፅ በስቁረተ እብንም ቢሉ አልፎ ሲሄድ ተገፎ ይወድቅለታል ይታደሳል ። እናንተም አርባ ብትጾሙ ተሐድሶተ ነፍስ ታገኛላችሁ ለማለት ። ምሳሌውን አውቆ አስመስሏል ፍጻሜው እንደም ነው ቢሉ አዳም በ፵ ቀን ያገኘውን ልጅነት አስወስዶ ነበርና ለሱ እንደካሰ ለማጠየቅ ፤ አንድም በ፵ቀን ተሰእሎተ መልክእ ለተፈጸመለት ሰው ሁሉ ሊካስ እንደመጣ ለማጠየቅ ። ፬ቱ ባሕርያት ዐሥር ዐሥሩን ለመካስ ። አምስተኛ ባሕርዩ ነፍስን የጨመሩ እንደሆነ ስምንት ስምንቱን ሊክስ እንደመጣ ለማጠየቅ ። ከዚህም ተራበ አልሳሳም ተዋጋ ድል አልተነሣም ወሰበ ጾመ እግዚእ ፵መዓልተ ወ፵ሌሊተ ከሠተ ከመ ኢሖመ ሥጋሁ እምረኃብ ወጽምዕ በኃይል ዘይደሉ ለመለኮት እንዲል ፤ ከዚህም ሥራውን ሠርቶ ሥሩ አለ እንጂ ። ባልዋለበት ጣት የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበት እንዲሉ ሳይሠራ እኛን ሥሩ አላለንም ወሐርን እግዚእ ለጹሰ ግብራት እንዲል ፷ ጌብራት የተባሉ ጥምቀት ፤ ተአምና ኃጣውእ ከዊነ ሰማዕት ተባሕትዎ ምንኵስና ። ጥምቀት በእደ ዮሐንስ መጠመቅ ተአምኖ ኃጣውእ ከተአማንያን ኃጣውእ ጋራ አንድ ሁኖ መቆጠር ከዊነ ሰማዕት እንስ በእንተ ዝንቱ ተወለድኩ ወእንበይነ ዝንቱ መጻእኩ ውስተ ዓለም ከመ እሙን ሰማዕተ በጽድቅ ብሎ ከጲላጦስ ፊት ቁሞ መመስከር ተባሕትዎ ፵ ቀን ዘምግብ ተከልክሎ በገዳም መኖር ፤ ምንኵስና በድንግልና መኖር ነው ። ረቂቅ ዘእምረቂቅ እንደሆነ ለማጠየቅ በጎቱም ድንግልና ተፀንሰ በጎቱም ድንግልና ተወለደ ። ዘኢይርኅብ እምዘኢይርኅብ እንደሆነ ለማጠየቅ ፵ መዓልት ፵ሌሊት ጾመ ዘኢይትገሠሥ እምዘኢይትገሠሥ እንደሆነ ለማጠየቅ በባሕር ላይ ሄደ ። ብርሃን ዘእምብርሃን እንደሆነ ለማጠየቅ ብርሃኑ መለኮቱን በደብረ ታቦር ገለጸ ሕይወት ዘእምሕይወት እንደሆነ ለማጠየቅ ያራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን አነሣ ። ወእምዝ ርኅበ ፤ ከዚህ በኋላ ተራበ ። ሐተታ ረኃቡም የፈቃድ ረኃብ ነው እጂ እንደኛ ረኃብ አይደለም እኛ ብንበላው ቁንጣን ብንተወው ስልት ቀጠና ይሆንብናል ፤ ረኀበ እግዚእነሰ አኮ ከመ ረኃበ ዚአነ አላ ገጸ ረኃቡ ፍሉጥ እምኔነ ለነሰ በግብር ይመውአነ ወሎቱሰ በፈቃዱ እንዲል ፤ አንድ ጊዜ ርኅበ አንድ ጊዜ ኢርኅበ ይላል እንደምነው ቢሉ ፤ ከ፪ት አካል ፩ አካል ከሁለት ባሕርይ ፩ባሕርይ እንደሆነ ለማጠየቅ ። በእንተ ምንት ርኅበ እግዚእነ ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ ያጠይቅ ከመ ውእቱ እም ፪ ህላዌያት እንዲል ። መራቡም ለእጽድቆተ ትስብእት ለካሣ ነው ።

፫ ወቀርበ ዘያሜክሮ ።

፫ የሚፈታተነው ዲያብሎስ ቀረበ ሐተታ እንዲያው አይቀርበውም ርኅበኩ የሚል ድምፅ ሰምቶት ፍሬ ዕፅ ሲሻ አይቶት ፤ መልኩን አጠውልጎ ታይቶት እሱም እንዲያው አይቀርብም በአምሳለ ሠዓሊ በአምሳለ ሐራሲ በቀዳዳ ሽልቻ ትኩስ ዳቦ የያዘ መስሎ ሁለት ደንጊያ ይዞ ይቀርባል አንዱን ባተ አንዱን ለኔ ዳቦ አድርገህ እንብላ እለዋለሁ ደንጊያውንማ ዳቦ ከማድረግ የያዝሽውን እንበላም ያለኝ እንደሆነ አዳምን አባቱን በመብል ምክንያት ድል እንደነሣሁት እሱንም በመብል ምክንያት ድል እነሣዋለሁ ብሎ ፤

ወይቤሎ እመ ወልደ እግዚአብሔር አንተ በል ከመ እላ እእባን ኅብስተ ይኩና ፤

በዮርዳኖስ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክርለት ሰምቶ ነበርና የእግዚአብሔርስ ልጅ ከሆንክ እነዚህ ደንጊያዎች ኅብስት ይሁኑ በልህ እዘዝ አለው ። ቢያደርገው የሰይጣን ተአዛዜ ብየ ዕዳ አልበታለሁ

ባያደርገው ደካማ እሰኝዋለሁ ። ቢያደርገው ሌላ ጾር እሻሊታለሁ ባያደርገው ድካሙን አይቼ እቀርባለሁ ብሎ ፣ ድንጊያውን ኅብስት አድርግ ማለቱ ምን ልማድ ይዞ ነው ቢሉ በዮሴፍ ልማድ ፣ ዮሴፍን አባቱ የሱን ስንቅ ለብቻ አሲዞ ለወንድሞችህ ስንቃቸውን ሰጥተህ ወንድሞችህን ጠይቀህ ና ብሎ ላከው ። ያሉበትን አጥቶ ሲፈልግ የሱ ስንቅ አለቀበት ከዚያ እንዳይበላ አባቱ ያላዘዘው ነው ። ረኃብ ጸንቶበት ሳለ መልአክ ያባትህን ፈጣሪ ድንጊያውን ዳቦ አድርግልኝ አትለውም አለው ። ወደ እግዚአብሔር ቢያመለከት ድንጊያው ዳቦ ሁኖለት ተመግቧልና እንዲህ አለ ።

፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ጌታም መለሰ ። ወይቤሎ ጽሑፍ ከመ አኮ በኅብስት ከመ ዘየሐዩ ሰብእ ። ዘዳ ፰ ፫ ሉቃ ፬፡፬ ።

፬ ሰው የሚድነው በኅብስት ብቻ እንዳይደለ ተጽፏል ።

አላ በኵሉ ቃል ዘይወፅእ እምአፉሁ ለእግዚአብሔር እግዚአብሔር ዳን ያለው ይድናል ሙት ያለው ይሞታል እንጂ ፣ አንድም ሰው የሚያድን ገብሬ በጻረበት በኅብስት ብቻ እንዳይደለ ተጽፏል ፤ እግዚአብሔር ምግብ ይሁን ያለውም ምግብ ይሆናል እንጂ እስራኤል ፵ ዘመን በትርህ አልወደቀ ጫማህ አልወለቀ ልብስህ አላለቀ እንዲሉ ከመትያናስ በደመና አይበት ተጋጥሮ በነፋስ ወደልጋዘ ተጭኖ መጠኑ ድንብላል አህሉ መልኩ በረድ መስሎ ወእንዘ የኃድጋህበ ይላል የውርጭ ገበታ ሲነጽፍ እየዘነመላቸው አርባ ዘመን ተመግበዋልና ፣ አንድም ሰው የሚድን ገብሬ በጻረበት በጋረበት በእንጀራ ብቻ እንዳይደለ ተጽፏል ፤ በዓቂበ ሕግም በትምህርትም ነው እንጂ ሐተታ ። የሰው ባሕርዩ ባሕርይ እንስሳዊ ባሕርይ መልአካዊ ነው ባሕርይ እንስሳዊ ምግብ ሲያጣ ይጎዳል ፣ ባሕርይ መልአካዊ ትምህርት ሲያጣ ይጎዳልና አእምር ከመ በእማን ሲያይ ቃለ እግዚአብሔር ሲሲተ ልብ ቃላቲሁ ለእግዚአብሔር ወእምጽእ ረኃበ እክል ወጽምዓ ማይ ሰብሐር ረኃብሰ እምሰሚዓ ቃለ እግዚአብሔር እንዲል ። አንድም ወልደ እግዚአብሔርስ ከሆንህ ይህ እንደ ድንጊያ ፈዞ ያለ ሰውነትህ ኅብስተ ሕይወት ኅብስተ መድኃኒት ይሁን ብለህ እዘዝ ሲያሰኘው ነው ። ጌታም ሰው የሚያድኝ በዕሩቅ ብእሲ ሥጋ እንዳይደለ ተጽፏል ። አካላዊ ቃል በተዋሐደው ሥጋ ነው እንጂ አለው ፭ ወእምዝ ነሥእ ወወሰዶ ውስተ ቅድስት ሀገር ።

፭ ከዚህ በኋላ ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ወሰደው ሐተታ እሱስ አይወስደውም ፈቃዱን ዐውቆ ስለሄደለት ካህናትን ድል ነሥቼበት በማላውቅ በገዳም ቢሆን ነው እንጂ ፣ ካህናትን ድል በምነሳበት በቤተ መቅደስ ቢሆን መች ድል ይነሳኝ ነበር ብሏል ፈቃዱን አይቶ ስለሄደለት ነሥአ ወሰዶ አዕረገ ይላል ወዓቀሞ ውስተ ተድባበ ቤተ መቅደስ ። ተድባብ ማዕዘንት ርእስ ይላል አብነት ፣ ተድባብ ያለ እንደሆነ ከዝንቦው ማዕዘንት ያለ እንደሆነ ከምሕዋሩ ርእስ ያለ እንደሆነ ከጉልላቱ አቀመው ። ከዚህም በአምሳለ ሊቀ ካህናት እምጭ ጠምጥሞ መነሳንስ ይዞ ይታየዋል ።

፮ ወይቤሎ እመሰ አማን ወልደ እግዚአብሔር አንተ ቅንጽ እምዝየ ወተወረው ታሕተ ።

፮ መዝ ፡ ፺፩ ።
በእውነት ወልደ እግዚአብሔር ከሆንህ ከዚህ ዘለህ ወደታች ውረድ አለው ፣ ሐተታ ቢሰበር ዐርፈዋለሁ ባይሰበር ምትሐት እሰኝዋለሁ ቢያደርገው ሌላ ጾር እሻሊታለሁ ባያደርገው ደካማ እሰኝዋለሁ ቢያደርገው የሰይጣን ተአዛዚ ብየ ዕዳ እልበታለሁ ባያደርገው ድካሙን አይቼ እቀርበዋለሁ ብሎ ነው ። እስመ ጽሑፍ ከመ ለመላእክቲሁ ይኤዝዞሙ በእንቲአከ ከመ ይዕቀቡከ በኵሉ ፍናዊከ በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክትን ሰላንተ እንዲያዛቸው ተጽፏልና ፤ ወበእደዊሆሙ ያነሥኡከ ከመ ኢትትዐቀፍ በእብን እግርከ እግረከ ይላል ፤ እግርህ እንዳይሰናከል፤በእጆቻቸውም ያነሡሃል የሚል ጽሑፍ አለና ፣ ጌታ ከላይ ጠቅሶበት ነበርና ፣ እሱም ፈንታውን ይንጉዳጉዳል ።

፯ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ካዕበ ጽሑፍ ኢታመክሮ ለእግዚአብሔር እምላክከ ።
፯ ፡ ዘዳ ፡ ፮ ፡ ፲፮ ።

ዳግመኛ ፈጣሪህን እግዚአብሔርን አትፈታተነው የሚል ጽሑፍ አለ አለው ፤ እንዲህ የሚል ከምን አለ ቢሉ እንደ ጊዜ ገድሉ ጠቀሰ ። እሥራኤል በገዳም ሳሉ ሙሴ ካሥራሁለቱ ነገድ አውጣጥቶ ኢያሱና ካሌብን ምድረ ርስትን ሰልላችሁኑ ብሎ ሰደዳቸው ። እሳቸውም ሰልለው ሲመለሱ ከወይኑ ዘለላ ከስንዴው ዛላ በባጢ ቀፎ ይዘው መጡ ። እንደምን ሁናችሁ መጣችሁ ሀገሪቱስ እንደምን ያለች ናት ብለው ጠየቋቸው ። ሀገሪቱስ መልካም ናት እንደዚህ ያለ ታፈራለች ፤ ባሕቱ ርኢነ ደቂቀ ሰኤናቅንኖሙ ከመ እርዝ ወጽንዖሙ ከመ አውልዕ ንሕነሰ ኮነ ከመ እናብጥ በቅድሜሆሙ ምድርኒ ትረድኦሙ ወተዓቅቦሙ ብለው ፲ሩ አስገርመው አስፈርተው ተናገሩ ካሌብና ኢያሱ በፈቃደ እግዚአብሔር እንገባታለን አሉ ፲ሩ ካገባንስ አሁን ያግባን ሙሴ ተነሣ ታቦተ ጽዮንንም አንሣ እንሂድ አሉት ፣ ሙሴ ታቦተ ጽዮንም አሁን አትነሣ እናንተም እግዚአብሔር ፈጣሪያችሁን አትፈታተኑት አላቸው ። አይሆንም ብለው ሄዱ ። በወሰን ያሉ አሕዛብ ገጥመው

ድል አደረጋቸው ፤ በዚህ ጊዜ ከባሕር ጠልቀው ። ከገደል ወድቀው አልቀዋል ፤

ከዚህም ጌታ አንደ ጊዜ ገድሎ ጠቀሰው ።

፰ ወእምዝ ነሥኦ ዲያብሎስ ወአዕረጎ ውስተ ደብር ነዋኅ ጥቀ

፰ ከዚህ በኋላ ወደ ረጅም ተራራ አወጣው ሐተታ ነገሥታትን ድል በማልነግበት በቤተ መቅደስ ቢሆን ድል ነግኝ እንጅ ፤ ነገሥታት ድል በምነግበት በተራራ ቢሆን መቸ ድል ይነግኝ ነበር ብኋል ፈቃዱን ዐውቆ ስለሄደለት አዕረጎ አለ ።

ወአርአዮ መንግሥታተ ኵሉ ዓለም ፤ ወኵሎ ክብሮ ፤ ጠጠሩን ወርቅ ብር ፤ ቅጠሉን ግምጃ አስመስሎ አሳየው አንድም መንግሥታተ ኵሉ ዓለም ። ግዛቱን ሁሉ አሳየው ወኵሎ ክብሮ እንስሳትን አራዊትን ፈረስ በቅሎ ሠራዊት አስመስሎ አሳየው ፤ እሱስ ያይለታል ቢሉ ስለመሰለው ነው እንጅ አያይለትም ድል መንሳቱ በምን ይታወቃል ቢሉ ባለመጽነኑ ።

፱ ወይቤሎ ዘንተ ኵሎ እሁበከ እምከመ ሰገድከ ሊተ ወአማኅከኒ ፤ ደፋር ነውና ብትሰግድልኝ እጅ ብትነሳኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው ።

፲ ወእምዝ ይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን ።

፲ ዘዳግም ፮ ፲፫ ፤ ከዚህ በኋላ ከኋላየ ወግድ አለው ራስ አይቶ የሚመጣ ጠላት ክፉ ነውና ጽኑ ባሳጋራዬ ሲል ነው ። ወዓቀመ አዴርሃ ሰይጣነ ሳዕለ ሰሎሞን እንዲል ። አንድም እምዘድኅሬየ ይላል አብነት ከኔ በኋላ ከሚነሱ ከምእመናን ወግድላቸው አለው ። እንዲህ ባለው ጊዜ እንደጢስ ተኖ እንደ ትቢያ በኖ ጠፍቷል ። ሐተታ እስካሁን ሑር አላለው አሁን ሑር ማለቱ ስለምን ቢሉ ፤ በቀዳሚ ጊዜ ጉየይ ወበካልዕ ጊዜ ጉየይ ወበሣልስ ተንሥእ ወተቃተል እንዲል ፤ አብነት ለመሆን በሦስተኛው ድል ንሱ ለማለት ንጉሥ በመንግሥቱ ጉልማሳ በሚስቱ እንዲቀና ፤ ጌታም ለአምልኮቱ ቀናዒ ነውና ፤ እስመ አነ እምላክ ቀናዒ ዘአፈዲ ኃጢአተ አብ ላዕለ ውሉድ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ለእለ ይጸልዑኒ ። ወለእለሰ ያፈቅሩኒ እገብር ምሕረተ እስከ ፲ቱ፱ ትውልድ እንዲል ።

ጽሑፍ ለእግዚአብሔር አምላክከ ትሰግድ ወኪያሁ ባሕቲቶ ታምልክ ፤ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ትሰግድ ዘንድ እሱንም ብቻ ታመልክ ዘንድ ተጽፏል አለው። ሑር እምድኅሬየ ባለው ጊዜ እንደጢስ ተኖ እንደ ትቢያ በኖ ጠፋ አላለምን ሰማን ይጠቅሰዋል ቢሉ ሰይጣንና ውሻ ምልልስ ወዳጅ ነውና ተመልሶ ያሰማዋል ። አንድም እንደ አምላክነቱ አጽንቶት ሰምቶ ይሄዳል ። አንድም ወጺጋሁ ታሰምዖ እንዲል ካለበት ሁኖ እንዲሰማው አድርጎታል ። አንድም ከሐተታ ለመዳን ጥቅሱ ይቀድማል ።

፲፩ ወእምዝ ኀደጎ ዲያብሎስ ።

፲፩ ከዚህ በኋላ ተወው እስከ ጊዜሁ ብሎ በሉቃስ ያቀናዋል ። በዕለተ ዓርብ በአይሁድ ሥጋው ሁኖ እስኪያሰቅለው ድረስ አይመለስበትም ። ከዚህም በኅ ልጅ ተወልዶ ለአዳምና ለሔዋን በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ነሣላቸው ። አሁን ዛሬ ደም ያለበት ሰው ጌሽ አስነሥቶ እምባውን ሰብሮ ደመኛውን ገድሎ ደሙን መልሶ ቢሄድ የቀሩት ከዛፍ ከገደል ተጠግተው የሆነስ ሆነ አንተ ማነህ እንወቅህ ባሉት ጊዜ የዘመዶቼን የእገሌ የእገሌ ደም የማይቀርብኝ እኔ እገሌ ነኝ ብሎ እንዲል ፤ ጌታም የአባቱ የአዳም የእናቱ የሔዋን ደም የማይቀርብኝ ሲል በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ነሣላቸው ፤ ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ስስት ትዕቢት ፍቅረ ንዋይ ናቸው ። ስስት ያልሰጡትን መሻት ነው ። ትዕቢት እምላክ እሆናለሁ ማለት ነው ። ፍቅረ ንዋይ በቃኝ አለማለት ነው ። በዚህ ሁሉ ድል ነሥቶታል ። ዛቲ ስፍጠት እንተ ረሰየቶ ለአዳም ይትመየጥ ውስተ መሬት ወሶበ በጽሐ ኀበ እምላኪየ ወኀበ ሲሳይ ለኵሉ ገብአ ሰይጣን ተኃፊሮ ወተመዊኦ

እንዲል ፡ አንድም ድል መንሳቱ ለአዳምና ለሔዋን ብቻ አይደለም ለሁሉም ድል ነሥቶላቸዋል የመነኩሳትም ጾራቸው ስስት ነው በሹት ጊዜ አያገኙትምና በትኅርምት ኑዋሪዎች ናቸው በቦታቸው በገዳም በስስት ቢመጣበት በትዕግሥት ድል ነሥቶላቸዋል የካህናት ጾራቸው ትዕቢት ነው አእምሯችን ረቂቅ ማዕርጋችን ምጡቅ እያሉ ይታበያሉ ። በቦታቸውም በቤተ መቅደስ በትዕቢት ቢመጣበት በትሕትና ድል ነሥቶላቸዋል ። የነገሥታት ጾራቸው ፍቅረ ንዋይ ነው ቤታቸውን ከፍ ካለ ቦታ ሠርተው ያለፈ ያገደመውን የወጣ የወረደውን እያዩ የዚህ ሁሉ እንጅ ኑሮው በኛ ነው እያሉ ገንዘብ ይሰበስባሉ ቦታቸው በተራራ ነው ። በተራራ በፍቅረ ንዋይ ቢመጣበት በጸሊዓ ንዋይ ድል ነሥቶላቸዋል ፤ ከዚህ በኋላ ኃጢአት ከሥሩ እንደተነቀለ ዛፍ ሁናለች ከሥሩ የተነቀለ ዛፍ እንዳይለመልም እንዳያብብ እንዳያፈራ ኃጢአትም በፍዳ የማታሲዝ ሆናለች ። ዛሬ የተያዙ አሉሳ ቢሉ አሊህማ ዐዋጅ አፍራሾች ናቸው ። ንጉሥ ይዘምታል ድል ነሥቶ ሲመለስ ከመንገድ የወጣህ ወታደር ብሎ ዐዋጅ ይነግራል በደለኛ ወታደር ገንዘብ ሲዘርፍ ከመንደር ገብቶ ቢሞት ንጉሥ ድል አልነሣም ይባላልን ? እኒህስ ዐዋጅ አፍራሾች ናቸው ።

ወናሁ መጽኡ መላእክት ይትለአክዎ ።

አርባ ቀን በትህርምት ኖሯልና መላእክት ኅብስት ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ ይዘው መጡ አንድም ድል

[illegible]ና ለኪ ኃይል ለከ ጸንዕ እያሉ እያመሰገኑ [illegible] ። እንደ ዓቢይ ንጉሥ እንደ ንዑስ ንጉሥ ተሰ[illegible] ። ከዚህ በኋላ ሠራዊታችን ለምን [illegible]ል አንድ ዓንድ እንገናኝ ብለው ተገናኙ ። ዓቢይ ንጉሥ ንዑስ ንጉሥን ገደለው ። የዓቢይ ንጉሥ ሠራዊት [illegible] እየዘፈኑ ተርበዋል ። የንዑስ ንጉሥ ሠራዊት [illegible] እያፈሩ ሸሽተዋል ። እኒህም ድል [illegible] ። [illegible] አለ ። ድል ከነሣ በኋላ [illegible] ቢሉ አስተድመው መጥ[illegible] ድል ነሣኝ እንጂ ብቻ [illegible] ድል ይነሣኝ ነበር ባለ ነበርና [illegible]ል ። እንድም እናንተም ድል ብትነሱ [illegible] ። አንዳንድ ባሕታዊ ሰይ[illegible] ይጠፋል አለው ። አልብየ ንጉሥ [illegible] ኢየሱስ ክርስቶስ አለው ፣ ይህ [illegible] ንጉሥ የለም ይላል ብሉ በያዘው [illegible]ል ። [illegible] መልአከ ዑቃ[illegible] እኔ መልአከ ዑቃቢህ [illegible] ። እንኪያ አስካሁን ወዴት ኖረሃል [illegible] ድል ብትነሣ ነው እንጂ ድል ባትነሣ [illegible] ነበር ብሉታል ።

[illegible] ነበረ እግዚእ ኢየሱስ በቅፍርናሆም ።

፲፪ [illegible] እግዚእ ኢየሱስ ከመ አኀዝዎ [illegible] ተግኅሠ ውስተ ገሊላ ። ማር ፩፡፲፬ ።

[illegible]

፲፫ [illegible] ናዝሬት ወመጽአ ኀደረ ቅፍርናሆም [illegible] ባሕር ።

፲፫ ናዝሬትን ትቶ በባሕር አጠገብ ባለች በቅፍርናሆም [illegible] ኖረ ። ውስተ አድባረ ዛብሎን ወንፍታሌም ። የዛብሎን የንፍታሌም ዕፃ በምትሆን

፲፬ [illegible] ይትፈጸም ዘተብህለ በኢሳይያስ ነቢይ

፲፬ በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል የተነገረው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ኖረ ።

፲፭ እንዘ ይብል ምድረ ዛብሎን ወምድረ ንፍታሌም ። ኢሳ ፱፥፩ ።

፲፭ በዛብሎን በንፍታሌም ዕፃ ያሉ ፍኖተ ባሕር ። በባሕር አጠገብ ያሉ ጺራልዩ ወጺራልያስ ። ጠጠር ገጠር ።
ማዕዶተ ሐይቀ ዮርዳኖስ ። በዮርዳኖስ ወደብ ማዶ በአንጻረ ሊባኖስ ያሉ ፣ ገሊላ ዘአሕዛብ የአሕዛብ ክፍል ዕፃ በምትሆን በገሊላ ያሉ ሐተታ ዘሕዝብ እለና ከዚያ ሲለይ ዘአሕዛብ አለ ፡ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን በሠራ ጊዜ ወአርድአ ኪራም በዕፀወ ቄድሮስ ወአውቄና እንዲል ፡ ጥድ ዘግባ እየጠረበ አግዞታል ሃያ ያህል ቀላል ቀላል አህጉር ሰጠው እሰመ ኢዓደማሁ ይላል ደስ ባያሰኙት ወዳጄ በኔና ባንተ ዘንድ ይህ ምን ቁም ነገር ነው አለው ። የመልክተኛ ማደሪያ ይሁንህ ብዬ ነው አለው ከዚህ በኋላ አሕዛብ እንደ ባለጉልት እሥራኤል አንደ ባለርስት ሁነው የሚኖሩ ሁነዋልና ገሊላ ዘአሕዛብ አለ ፤ አንድም ፈርዖን አሕዛብን ወግቶ ለልጁ ለሰሎሞን ሚስት ሰጥቷት ነበርና ገሊላ ዘአሕዛብ አለ ።

፲፮ ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእየ ብርሃነ ዓቢየ ፤

፲፮ በጨለማ ያሉ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን ወጣላቸው ። ወለእለሂ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ብርሃን ሠረቀ ሎሙ በጨለማ በሞት ጥላ ለሚኖሩ ብርሃን ወጣላቸው ብሎ ኢሳይያስ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ በቅፍርናሆም ኖረ ። አንድም በድንቁርና በቀቢጸ ተስፋ ለነበሩ ሰዎች ዕውቀት ተሰጣቸው ፣ አንድ ገጽ በማለት ሞትን በመምሰል ሞት ባመጣው ምስል ለሚኖሩ ሰዎች ክርስቶስ ተወለደላቸው ወንጌል ተጻፈላቸው ።

አንድም በሞተ ሥጋ በሞተ ነፍስ ለነበሩ ልጅነት ተሰጣቸው ። በኃጢአት በክህደት ለነበሩ ሃይማኖት ተገለጸላቸው ። ሐተታ ኃጢአትን ጽልመት ክህደትን ጽላሎተ ሞት አለው በጨለማ ላይ የጣፍ የገደል ጥላ የተጨመረ እንደሆነ ጨለማው እንዲጠና በኃጢአትም ላይ ክህደት የተጨመረ እንደሆነ ፍዳው ይጸናልና ፤

፲፯ ወእምአሜሃ አኀዘ እግዚእ ኢየሱስ ይሰብክ ወይብል ነስሑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ። ማር ፩፡፲፬ ።

፲፯ ዮሐንስ ከተጋዘበት ቀን ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደጊቱ በልጅነት ልጅነት በሃይማኖት ልትሰጥ ቀርባለችና እመኑ እያለ ያስተምር ጀመረ ዮሐንስ ከተጋዘ በኋላ ማስተማሩ ስለምን ቢሉ መምር ሳለ በመምር ላይ አናስተምራለን አትበሉ ለማለት ። አንድም መምሩ አንድ ዮሐንስ ነበረ ያውም ተመተረ እንዳይሉ ትምህርቱንም አሰወጠውም ያስንቱን ይሰሟል እንዳይሉ ፣ አንድም ዮሐንስ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ብሉ ያስተማረልኝ እኔ ነኝ ሲል ነው ፡ ነያ ይሰምያ መንግሥተ ሰማያት ለአስተርእዮቱ ማእከለ ፍቁራኒሁ እንዲል ።
በአንተ ቀዳማውያን ሐዋርያት

፲፰ ወእንዘ ያንሶሱ መንገለ ባሕረ ገሊላ ርእየ ፪ተ አኃወ ። ማር ፩፡፲፮ ።

፲፰ በገሊላ ባሕር ማዶ ሲመላለስ ሁለት ወንድማማቾች አገኘ ። ስምአንሃ ፡ ዘተሰምየ ጴጥሮስ ። ጴጥሮስ የተባለ ስምአንን ። ወእንድርያስሃ እኀዋሁ

ወንድሙን እንድርያስን እንዘ ይወድዩ መርበብቶሙ ውስተ ባሕር ፤ መረባቸውን ከባሕር ሲጥሉ እስመ መሠግራን እሙንቱ ዓሣ ወጋሮች ነበሩና ።

፲፱ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ንዑ ትልውኒ ድኅሬየ ።

፲፱ ለጊዜው በእግር ተከተሉኝ ፍጻሜው በግብር ምሰሉኝ አላቸው ወእሬስየክሙ መሠግራነ ሰብእ ሰውን እንደ ዓሣ ወንጌልን እንደ መረብ ይህን ዓለም እንደ ባሕር አድርጋችሁ እንድታስተምሩ እደርጋችኋለሁ አላቸው ።

፳ ወበጊዜሃ ኀደጉ መሠግሪሆሙ ወተለውዎ

፳ ያን ጊዜ ፈጥነው መርከባቸውን መረባቸውን ትተው ተከተሉት ለጊዜው በእግር ተከተሉት ፍጻሜው በግብር መሰሉት ።

፳፩ ወተዓዲዎ ሕቀ እምህየ ርእየ ካልዓነ ፪ተ አኃወ ።

፳፩ ከዚያ ጥቂት እልፍ ብሎ ሁለት ወንድማማች አገኘ ፤ ያዕቆብሃ ወልደ ዘብዴዎስ ወዮሐንስሃ እኅዋሁ ፤ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብን ወንድሙ ዮሐንስን ፤ ውስተ ሐመር ምስለ ዘብዴዎስ አቡሆሙ ፤ ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋራ እንዘ ይሠርዑ ወያስተማንዩ መሣግሪሆሙ ።

መረባቸውን ያደፈውን ሲያጥቡ የተቀረጠውን ሲቀጥሉ ፡ ወጸውዖሙ ። ለጊዜው በእግር ተከተሉኝ ፍጻሜው በግብር ምሰሉኝ አላቸው ።

፳፪ ወበጊዜሃ ኀደጉ ሐመሮሙ ወዘብዴዎስሃ አባሆሙ ወተለውዎ ።

፳፪ ያን ጊዜ ፈጥነው መረባቸውን መርከባቸውን ዘብዴዎስ አባታቸውን ትተው ተከተሉት ፤ ሐተታ ፡ አክብር አባከ ወእመከ ይል የለም ቢሉ ። ይህን ቃሉ ካልተማሩ አያውቁትምና ። አንድም ከአክብሮተ አብ ወእም አክብሮተ እግዚአብሔር እንዲበልጥ ለማጠየቅ ። አባትን የሚረዳው ልጅ የሚረዳበት ገንዘብ ያለ እንደሆነ ትቶ መሄድ ይገባል ። የሚረዳው ልጅ የሚረዳበት ገንዘብ የሌለው እንደሆነ ትቶ መሄድ አይገባም እሱን ግን ምስለ አሳቡ ብሎ በማርቆስ ያቀናዋል ገንዘብ ያለው ነው ።

በእንተ ቀዳማዊ ስብከቱ ወመንክራቲሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፳፫ ወአንሶሰወ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ኵሉ ገሊላ እንዘ ይሜህር በምኩራባቲሆሙ ።

፳፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምኵራብ ገብቶ ሲያስተምር በገሊላ ሲመላለስ ኖረ ።
ወይሰብክ ወንጌለ መንግሥት ፡ ጌትነቱን የምትናገር ወንጌልን እያስተማረ ኖረ ። ሐተታ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር እንደነገሠ ዲያብሎስ እንደተሻረ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደጠፋ ትናገራለችና ወንጌለ መንግሥት ይላታል ወይፌውስ ኵሎ ድውያነ ወኵሎ ሕሙማነ ዘውስተ ሕዝብ ለዚህም ምልክት በሕዝቡ ዘንድ ያሉ ድውያንን ሁሉ ይፈውስ ነበረ ።

፳፬ ወወፅአ ስሙዓተ ነገሩ ውስተ ኵሉ ሶርያ

፳፬ የተአምራቱ ዜና በሶርያ በ፬ቱ መዓዝን ተነገረ ።

ወአምጽኡ ኀቤሁ ኵሎ ድውያነ ወኵሎ ሕሙማነ ዘሰሰዚአሁ ሕማሞሙ ።
ደዌያቸው ልዩ ልዩ የሚሆን ድውያንን ወደሱ ይዘው መጡ ወዲዑራነ፤ ወእለሂ ቦሙ አጋንንት ።
የተጨነቁትን ። አጋንንት ያደሩባቸውን ። ወወርኃውያነ ፤ ሠርቀ ወርኅ እያየ የሚጥላቸውን ፡ ጨረቃ እንጂ ባታመልኩ ነው ሰሚሰት ፤ አንድም ምልእተ ወርኅ ሲሆን ደም ይመላል ብርድ ብርድ ይላል ደዌ ይቀሰቅሳልና ።
ወእለሂ ነገርጋር ።

ድልስጣ የሚባል ጋኔን አለ አንድ እግሩን ወደ ላይ አንድ እግሩን ወደታች አድርጎ ሲታያቸው ይጥላቸዋልና ።
ወመፃጉዓነ ።
የጸናባቸውን ።
ወአሕየዎሙ ፤
እነዚህን ሁሉ አዳናቸው ፤

፳፭ ወተለውዎ ብዙኃን አሕዛብ እምገሊላ ወእምዓሥርቱ አህጉር ወእምኢየሩሳሌም ወእምይሁዳ ወእማዕዶተ ዮርዳኖስ ። ማር ፫ ፡ ፯ ፡ ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ።

፳፭ ካሥር አህጉር ከብዙ መንደር ተወጣጥተው አምስት ገባያ ያህል ሰዎች ተከተሉት ፣ ላንድ ሽማግሌ ዐሥር ልጆች ነበሩት እኒህ እየራሳቸው አንድ አንድ አገር አቅንተው ይኖሩ ነበርና ፡ አንድም ጲላጦስ ለቀረጥ ይመቸኝ ብሎ አንዱን ከተማ ካሥር ከፍሎታል ፡ ከዚህ ተወጻጽተው ተከትለውታል እነዚህም ስለ አምስት ነገር ይከተሉታል ፡ አንዱ ገባያ መልኩን እናያለን ብለው ፡ አንዱ ገበያ ኅብስት አበርክቶ ያበላናል ብለው ፣ አንዱ ገባያ ትምርቱን እንሰማለን ብለው ፡ አንዱ ገባያ ከደዌያችን ይፈውስናል ብለው ፤ አንዱ ገባያ የአሪትን መፍረሻ የወንጌልን መታነጫ እናያለን ብለው ነው ። ለኒህም ትንቢት ተነግሮላቸዋል ተነግሮባቸዋል ። መልኩን እናያለን ላሉት ይሜኒ ላሀዩ እምውሉደ ዕጓለ እመሕያው ተብሎ ፤ ኅብስት አበርክቶ ይመግበናል ላሉት ወኢያንጥአሙ እምዘፈቀዱ ተብሎ ፡ ያስተምረናል ላሉት ጥዑም ለጉርዔየ ነቢብከ ተብሎ ። ከደዌያችን ይፈውሰናል ላሉት ነሥአ ደዌነ ወጾረሕማመነ ተብሎ

የኦሪትን መፍረሻ የወንጌልን መታነጫ እናያለን ባሉት ቅንዓት አንዮሙ ሰሕዘብ አብዳን ተብሎ ተነገርባቸዋል ። እኒህንም ባምስት ነገር ይፈውሳቸዋል በሐልዮ በነቢብ በገቢር በዘፈረ ልብስ በወራቀ ምራቅ ኀቢር ኩሉ ይገባል ።

በእንተ ብፁዓን ።

ምዕራፍ ፭ ።

፩ ወርእዮ ብዙኃነ አሕዛብ ዓርገ ውስተ ደብር ወነበረ ።

፪ ወሶበ ርእየ ይላል ፣ ብዙ ሰዎችን ባየ ጊዜ ከተራራ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ ። ሐተታ ፣ ምነው አሕዛብ አላቸው እስራኤል አይደሉም ቢሉ ብዛታቸውን ሲያይ ፣ አንድም ግብረ አሕዛብን ይሠራሉና ፀጸያፍ የገባ ሰው ሲበዛ ከመርከብ ከተራራ ሁኖ ማስተማር ልማድ ነው ። መምህር ከፍ ካለ ቦታ ሰማዕያን ዝቅ ካለ ቦታ የሆኑ እንደሆነ ትምህርት ለሰማዕያን ይረዳልና ፣ ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ እንዲል ። አንድም በደብረ ሲና ሕገ ኦሪትን የሠራሁ እኔ ነኝ ሲል ። አንድም ልዑለ ባሕርይ ነኝ ሲል ። አንድም የሠራሁላችሁ ሕግ ልዕልት ናት ። እናንተም ሉዓላውያን ናችሁ ሲል ።

ወቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ ። ደቀ መዛሙርቱ ወደሱ ቀረቡ ። የቀረው ግን የራቀውም ርቆ የቀረበውም ቀርቦ ይሰማል እኒህ ግን መደበኞች ናቸውና ትምህርት የሚቀር በኒህ ነውና፣ አንድም ለጉባኤው ሥፍራ አለውና ፤ ጥንተ ቀራቦች ናቸውና ቀረቡ ።

፫ ወከሠተ አፉሁ ።

፫ ነገር ጀመረ ፤ ወከሠተ አፉሁ ኢዮብ ወረገማ ለዕለት እንተ ባቲ ተወልደ ። ወከሠተ አፉሁ ጴጥሮስ ወአኀዘ ይንግሮሙ እምቀንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ። ወከሠተ አፉሁ ፊልጶስ ወአኀዘ ይንግሮሙ በውእቱ መጽሐፍ እንዲል ።
ወመሀሮሙ እንዘ ይብል ።

እንዲህ ብሎ አስተማራቸው ፤ ሐተታ እስከ አሁን ያምስት ገብያ ሰው ይከተለው ነበር ከእንግዲህ ወዲህ በብፁዓን ዓዋጅ ይለያቸዋል ። ንጉሥ መንግሥቱ እስኪደላደልለት ድረስ ሌባ ወምበዴ ይከተለዋል ። መንግሥቱ ግን ከተደላደለ በኋላ ሌባ ወንበዴ ተለይ ብሎ ዓዋጅ እንዲነግር ፣ በብፁዓን ዓዋጅ ይለያቸዋል

፫ ብፁዓን ነዳያን በመንፈስ ። ሉቃ ፮ ፣ ፳ ። ብፁዓን እለ ያነድዩ ርእሶሙ ይላል ።

፫ አውቀው ከብዕል ነዳያን ነን የሚሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፣ ብዕል እንጂ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው ለኛስ ባሕርይ የሚስማማው ንዴት ነው ብለው ብዕሉም እንደ ኢዮብ እንደ አብርሃም ነው አንድም ከጥበብ ነዳያን ነን የሚሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ጥበብ እንጂ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው ለኛስ ባሕርይ የሚስማማው ድንቁርና ነው ብለው ጥበቡም እንደ ሲራክ እንደ ሰሎሞን ነው። አንድም ከአእምሮ ነዳያን ነን የሚሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው መኰንኑ ተሰሎንቄ አፈወርቅን እንደጠየቀው ፣ ቅዱሳን ከበቁ በኋላ ከአእምሮ ነዳያን ነን ማለታቸው እንደምነው አለው ፣ አንተ በሀገርህ እንደምን ትኖራለህ አለው ፣ ከሁሉ በላይ ነኝ አለው ። እልፍ ብለህ በቂሳርያስ አለው የምበልጣቸውም አሉ፣ የሚተካከሉኝም አሉ አለው ። እልፍ ብለህ ቁስጥንጥንያ አለው የሚበልጡኝም አሉ የምተካከላቸውም አሉ አለው ። ዝቅ እያለ ሂደ ። እልፍ ብለህ በአንጾኪያ አለው ። ከዚያስ እንዳለሁም እንደ ሌላሁም የሚያውቀኝ የለም አለው ። ቅዱሳንም ከአእምሮ ነዳያን ነን ማለታቸው በበላያቸው ያለውን እያዩ ነው ብሎታል ። አንድም በመማር በማርስተማር በምናኔ በንስሐ በሃይማኖት ነዳያን ነን የሚሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው እስመ ሎሙ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት ።

መንግሥተ ሰማያት የሳቸው ናትና ማለት መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉና ፣

፬ ብፁዓን እለ ይላህው ይእዜ ።

፬ መዝ ፴፮፣፲፩ ዛሬ የሚያዝኑ የሚያለቅሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። ሐተታ ፣ የሚገባ ኃዘን የማይገባ ኃዘን አለ ። የማይገባ ኃዘን እናት አባት ሞተብኝ እኅት ወንድም ዘመድ የለኝ ርስት ጉልት ሄደብኝ ብሎ ማዘን አይገባም ። እንዳባት እንደናት ሥሳቤ እንደ ወንድም እንደ እኅት መላእክት አሉና እንደ ርስት እንደ ጉልት የማታልፍ ርስት ጉልቅ መንግሥተ ሰማይ አለችና ፣ የሚገባ ኃዘን የራሱን ኃጢአት አስቦ የባልንጀራውን ኃጢአት አይቶ ግፍዓ ሰማዕታትን ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን አስቦ ማዘን ይገባል ። የራስን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን እንደ አዳም እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ዳዊት ነው ፣ መልካቸው ሳይለወጥ ሳይሰቀቁ ዕንባቸው እንደ ሰንውኃ ይወርድ ነበር ። የባልጀራውን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን እንደ ሳሙኤል ነው እስከ ማዕዜኑ ትላሕዎ ሳሙኤል ለሳኦል እስመ አነ መነንክዎ ወገደፍክዎ ። ወሶበ ርእያ ለሀገር በከየ ላዕሌሃ ወሶበ ርእዮ ለዘያገብእ ተሀውከ በመንፈሱ እንዲል ፣ ግፍዓ ሰማዕታትን አስቦ ማዘን እንደ እስጢፋኖስ ። ወለእስጢፋኖስሰ ነሥእዎ ዕደው ጻድቃን ወቀበርዎ ወለሀውዎ ዓቢየ ላሐ እንዲል ። ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን አስቦ ማዘን እንደ ዮሐንስ ነው የዕለተ ዓርብ መከራውን እያሰበ ፸ ዘመን ቈጹረ ገጽ ሁኖ ኑሯል ። አንድም ዛሬ በንስሐ የሚያለቅሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እስመ እሙንቱ ይትፌሥሑ ፤ የኃዘን አጸፋው ደስታ ነውና ይትፌሣሑ አለ እንጂ መንግሥተ ሰማይን ይወርሳሉና ሲል ነው ።

፫ ብፁዓን የዋሀን ፡

፭ ኢሳ ፲፩፥፬ ኃደግያን በቀል የሆኑ ከየውሃት ጠባይዓዊ የደረሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። አንድም ሰውነታችንን መክረን አስተምረን ማኖር እንደምን ይቻለናል ብለው በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖሩ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው እስመ እሙንቱ ይወርስዋ ለምድር ።

ምድር መንግሥተ ሰማይን ይወርሳሉና ። ሐተታ ምድር አላት ይህ አልፎ በዚህ የምትተካ ስለሆነች ምድራውያን ጻድቃን የሚወርሷት ስለሆነ ። በምድር በሠሩት ሥራ የምትወረስ ስለሆነች ፤ በምድር ተድላ ሥጋ እንዲፈጸም ። በመንግሥተ ሰማይም ተድላ ነፍስ ይፈጸማልና ፤ ወሥርዓተ እግዚአነስ እሰፌወነ በብሂሎቱ ብፁዓን የዋሀን እስመ እሙንቱ ይወርስዋ ለምድር ከመ ሎሙ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት እንዲል ።

፮ ብፁዓን እለ ይርኀቡ ወይጸምዑ በእንተ ጽድቅ ።

፬ እብዝተንማ ከተመገብን ሰውነታችንን ወስኖ ገቶ ማኖር እንደምን ይቻለናል ብለው ከሚበሉት ከሚጠጡት ከፍለው የሚራቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እስመ ሙሉ ዘያነዲ ርእሶ እምነ መበልዕት ብዙኃት ውእቱ ይክል እኂዞተ ሥጋሁ እንዲል ፤ አንድም ጨርሰንማከተመገብነ መንግሥተ ሰማያትን በምን እንዋጃታለን ብለው ከፍለው ለነዳያን ሰጥተው የሚራቡ የሚጸሙ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ አንድም ከመብልዓ ኃጢአት የሚራቡ ከስቴ ኃጢአት የሚጸሙ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ አንድም ለፍቅሩ የሚሳሱ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። ጸምዓት ነፍስየ ለከ እንዲል ፤ አንድም በመማር በማስተማር በሃይማኖት በምናኔ በንስሐ የሚራቡ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እስመ እሙንቱ ይጸግቡ ። የረኃብ አጸፋው ጽጋብ ነውና ይጸግቡ አለ እንጂ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉና ሲል ነው ይጸምዑ ባለው ዐጸፋ ይረውዩ የሚል ይገኛል ።

፯ ብፁዓን መሀርያን ፤

፭ ለሰው የሚያዝኑ የሚራሩ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። ሐተታ ምሕረት ሥጋዊ ምሕረት መንፈሳዊ ምሕረት ነፍሳዊ አለ ምሕረት ሥጋዊ ቀዶ ማልበስ ቆርሶ ማጉረስ ቢበድሉ ማሩኝ ቢበደሉ ይቅርታ ነው ምሕረት መንፈሳዊ ፤ ክፉው ምግባር በጐ ምግባር መስሎት ይዞ ሲኖር መክሮ አስተምሮ ክፉውን ምግባር አስትቶ በጐውን ምግባር ማሠራት ነው ምሕረት ነፍሳዊ ክፉው ሃይማኖት በጐ ሃይማኖት መስሎት ይዞት ሲኖር ክፉውን ሃይማኖት አስትቶ በጎውን ሃይማኖት ማስያዝ ነው ፤ አንድም ምሕረት ሥጋዊ አይሰወጥም ምሕረት መንፈሳዊ ክፉውን ሃይማኖት ክፉውን ምግባር በጎ ምግባር ሃይማኖት መስሎት ይዞት ሲኖር መክሮ አስተምሮ ክፉውን ሃይማኖት አስትቶ በጎውን ማስያዝ ክፉውን ምግባር አስትቶ በጎውን ማሠራት ነው ። ምሕረት ነፍሳዊ መጥዎተ ርእስ ነው ። ታሪክ እንደ አንጢላርዮስ እንደ እሁ ቅዱስ ይህ አንጢላርዮስ ባለጸጋ ነው ንፉግ ነው ፤ ነዳያን ሲያልፉ አይተው ይህ ጽኑ ጨካኝ ባለጸጋ ለሰው አያዝንም አሉ አንዱ እኔ ፪፻ ሰጥቶኝ በልቼ ብመጣስ ብትመጣስ ተወራርዶ ሂዷል ምግቡን አቅርቦ እጁን ታጥቦ በሚመገብበት ጊዜ ስመ እግዚአብሔር ጠራበት እንዳ ይሰጠው ተርቧል እንዳይነሣው ስመ እግዚአብሔር ጠራበት ተናዶ ዳቦውን ወርውሮ ግንባሩን ገመሰው ደሙን አብሶ ዳቦውን ጎርሶ ለምልክት ጥቂት ይዞ ሄደ ። በዚህ ሌሊት ራእይ ያያል ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ መላእክተ ጽልመት እያዳፉት ይዘዋት ሲሄዱ መላእክተ ብርሃን ሲከተሏት እናንተ ከዚህ ምን አላችሁ ሲሏቸው ምነው ትላንት ለድኃ ሰጥቶ የለም ይሏቸዋል መታው እንጂ መቸ ሰጠው አላቸው ይመስክር ተባብለው መጥተው መስክር አሉት ኦ ባዕል ትማልም ዘአጽገብከኒ እምጽኡከኑ ዝየ ወኢተዓውቀኒ ደም እምጽንፃ ረኃብ ብሎ መስክር ሲያስለቅቃት መላእክተ ብርሃን እጅ ሲያደርጓት አየ ፤ ሲነጋ በዚህ ዓለም ሳሉ በገንዘብ ቢያውቁበት እንዲህ ያለ ጥቅም አለን ብሎ ነዳያንን ሰብስቦ ያለ ገንዘቡን ጨርሶ መጽውቶ ሲሄድ ነዳያን ከመንገድ አገኙት ገንዘብ ትሰጣለህ ቢሉን መጥተን ነበር አሉት ቀደም ብላችሁ መጥታችሁ ቢሆን ከፍየ እሰጣችሁ ነበረ አሁንማ ጨርሻለሁ አላቸው ፤ እንደምን እንሁን እሉትእኔን ሸጣችሁ ተካፈሉ አላቸው ለ፴ ወቄት ሸጠውታል ፤ ከተሸጠበት አገር ከብት ያውላል ማታ የሚያልበው ደም ይሆናል በዚህ ሰው እጅ ለመረዳት አልበቃችሁም ለማለት ሲያርስ ውሎ ማታ ሣሩን እለምልሞ ውኃውን አፍልቆ ይመግባቸዋል በዚህ ዕጹብ ዕጹብ ሲሉ ከተወለደ ጀምሮ ተናግሮ የማያውቅ ድዳ ሰምቶ የማያውቅ ደንቆሮ ነበር እፍ ቢለው ድዳው ተናግሯል ደንቆሮው ሰምቷል በዚህ ዕጹብ ዕጹብ ሲሉ ተሰውሯል ።

እኑ ቅዱስ በአሕዛብና በክርስቲያን መካከል ባለች በወሰን አገር ኤጲስቆጶስነት ተሹሞ ይኖራል። አሕዛብ ክርስቲያንን እየማረኩ ሲወስዱ ገንዘብ

እየሰጠ ይመልሳቸዋል እንዲት ድኃ ልጁዋ ተማሬ ከባት መጥታ ገንዘብ ስጠኝ አለችው ገንዘቤን ጨርሻለሁ እኔን ተከተሽ ልጅሽን መልሺ አላት ። እሱን ተከታ ልጁዋን መልሳለች ከሄደበት አገር የንጉሡ ልጅ ሞተችበት ኃዘን እንደጸናበት አይቶ ልጅህን ባነሣልህ ምን ባደረግህልኝ አለው የመንግሥቴንም እኩሌታ ቢሆን እሰጥሃለሁ አለው ይህንንስ አልሻም ከኔም አስቀድሞ ከኔም በኋላ የተማረኩትን ክርስቲያን ትሰጠኝ እንደሆነ ሳሥንሣልህ አለው ፤ ይሁንልህ አለው አሥነሥቶት ከሱም አስቀድሞ ከሱም በኋላ የተማረኩትን ክርስቲያን ይዞ ወጥቷል ፤ በዚህም ጌታን መስሎታል ጌታ እሱ ሰው ሳይሆን ከሱ አስቀድሞ የነበሩትን ሰው ከሆነም በኋላ ቢአል የወረዱትን ፭ድቀን በዕለተ ዓርብ ይዞ ለመውጣቱ ምሳሌ እንድም በንስሐ ለሰው የሚያዝኑ ቀሳውስት ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እስመ ሎሙ ኪ ይምህርዎሙ ፤

ለሳቸውም ሥላሴ ያዝኑላቸዋል ይራሩላቸዋልና ።

፰ ብፁዓን ንጹሐን ልብ ፤ መዝ፡ ፳፫ ፤ ፬ ።

፰ ከንጹሐን ልቡና የደረሱ እንድም በንስሐ ከኃጢአት ንጹሐን የሆኑ ፥ እንድም ከቂም ከበቀል ንጹሐን የሆኑ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ እስመ ዘያነብር ቂመ ውስተ ልቡ ኢውክፍት ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር ጸሎቱ ለመስተቀይም ከመ ዘርዕ ዘወድቀ ማእከለ አሰዋክ እንዲል ።

እስመ እሙንቱ ይሬእይዎ ለእግዚአብሔር ።

ሰውነታቸው ጸርቶላቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና እስመ በኢንጽሐ መንፈስ ርእይዎ ነቢያት ለእግዚአ ብሔር ወተናጸሩ ገጸ በገጽ እንዲል ። እስካሁን ይሬእይዎ እላለ አሁን ይሬእይዎ አለ ምነው ቢሉ በኒህ ማየት የሁሉን መናገር ነው ።

፱ ብፁዓን ገባርያነ ሰላም ።

፱ እብነት እለ ይገብሩ ሰላመ ይሳል ፤ አቀበቱን ወጥተው ቍልቍለቱን ወርደው ሰውን ከሰው ጋራ የሚያስታርቁ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፤ እንደ መልከ ጼዴቅ እንደ ሊቀ ሀገር የመልከ ጼዴቅ በጳውሎስ ታውቋል፤ ሊቀ ሀገር ሦስት ልጆች ነበሩት።አንተ ይህን ሥራ አንተ ይህን ሥራ ብሎ እዝዞ እሱማን ከማን ተጣልቷል እያለ እየዞረ ሲያስታርቅ ይውል ነበር ። እንድም ሰው ሰርቆ ቀምቶ ከፈጣሪው ጋራ የሚጣላ የሚበላው የሚለብሰው እንጂ ቢያጣ ነው ብለው የሚበላውን የሚለብሰውን ሰጥተው ከእግዚአብሔር ጋራ የሚያስታርቁ ባለጠጎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው እንድም ሰውን በንስሐ ከእግዚአብሔር ጋራ የሚያስታርቁ ቀሳውስት ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። እስመ እሙንቱ ውሉደ እግዚአብሔር ይሰመዩ ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና እስካሁን ውሉደ እግዚአብሔር አላለም አሁን እንዲህ ማለቱ ስለምን ቢሉ በመሰሉት ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ ወደ መቃብር ወርዶ ሰውን ከእግዚአብሔር እንዳስታረቀ እሳቸውም አቀበቱን ወጥተው ቍልቍለቱን ወርደው በማስታረቃቸው ይመስሉታልና በኒህ መምሰል የሁሉንም መምሰል መናገር ነው ።

፲ ብፁዓን እለ ይሰደዱ በእንተ ጽድቅ። ፩፡ጴጥ፡ ፪ ፡ ፳ ፫ ፡ ፲፬ ፬ ፡ ፲፬

፲ በመማር በማስተማር በምናኔ በንስሐ በሃይማኖት እገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ። እስመ ሎሙ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት

መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉና ፥ በመጀመሪያ ተናግሯት ውስጥ ለውስጥ ቢናገራት መጥቶ ነበርና በ፰ኛው እነሣት በመጀመሪያ ማንሣቱ ለአዳም እንደ ተሰጠች ለማጠየቅ በ፰ኛው ማንሣቱ በ፰ኛው ሺህ ለሁሉ እንድትሰጥ ለማጠየቅ ።

፲፩ ብፁዓን አንትሙ ሶበ ይሰድዱክሙ ።

፲፩ ከሀገራችሁ አስወጥተው ቢሰዷችሁ ንዑዳን ክቡራን ናችሁ ወይዘነጕጕክሙ ።

ዓብዳን ዝንጉዓን ጊጉያን ርጉማን ሰሑታን ቢሏችሁ ወይነቡ ኵሎ እኩየ ላዕሌክሙ እንዘ ይሔስው በእንቲእየ ።

በኔ ስም ስላመናችሁ በኔ ስም ስለተጠራችሁ በኔ ስም ስላስተማራችሁ ፡ በሐሰት ክፉውን ነገር ቢናገሩባችሁ ።

፲፪ ተፈሥሑ ወተኀሠዩ ።

፲፪ ፈጽሞ ደስ ይበላችሁ ።

እስመ ብዙኅ እሤትክሙ በሰማያት ።

ዋጋችሁ በኔ ዘንድ ፍጹም ነውና ካሥሩ ቃላት እንጸ ጽሮ ዐሥሩን ብፁዓን ተናገረ ዐሥረኛውን በዮሐንስ ያመጣዋል ። ሙሴ ዘጠኙን ቃላት በአሪት ዘፀአት ተናግሮ ዐሥረኛውን በአሪት ዘሌዋውያን እንዳመጣው ።

እስመ ከማሁ ሰደድዎሙ ለነቢያት እለ እምቅድሜ ክሙ ።

ከናንተ አስቀድሞ የነበሩ ነቢያትን ከሀገራቸው አስወጥተው ይሰዷቸው ነበርና ፤ ይሰድዱክሙ ሻለው እንድም መከራስ እንቀበል ብንል ማን እብነት ይሆንናል ትሉኝ እንደሆነ ከናንተ አስቀድሞ የነበሩ ነቢያትንም እንጂ ነቢያትንም እኮን ከሀገራቸው አስወጥተው ይሰዷቸው ነበር ፥ እኒያ እብነት ይሁኑ ዋችሁ ።

በእንተ ሐዲስ ኪዳን ተእርዮታ ምስለ ብሊት ፥

፲፫ እንትሙ ውእቱ ጼው ለምድር ማር ፱ ፵፱ ሉቃ ፲፬ ፡ ፴፬ ።

፲፫ በዚያውም ላይ የሰው አብነቱ እናንተ ናችሁ ወእመሰ ፄው ለሕሐ በምንት እንከ ይቄሰምዎ ።

ጨው ጣዕም ባይኖረው በምን ያጣፍጡታል ፣ ራሱን እንድም አፍርጁን ሽንኩርቱን በምን ያጣፍጡታል ፤ አልቦኬ እንከ ዘይበቍዕ ።

የሚረባው የሚጠቅመው የለም ለአፍርጁ ለሽን ኩርቱ ፣ እንድም ሲራሱ የሚያገኘው ረብሕ ጥቅም የለውም ።

ዘእንበለ ዘይገድፍዎ አፍአ ።
አፍአ አውጥተው ይጥሉታል ወይከይድዎ ሰብእ በአ ገሪሆሙ ሰዎች በእግራቸው ይጠቀጥቁታል እንጂ ፤ ሐተታ ቢከቡት ይናዳል ቢንተራሱት ራስ ይመል ጣል ከተክል ቦታ ቢያደርጉት ተክል ያደርቃል ብለው እንድም አንትሙ ውእቱ ፄው ለም ድር የሰው አብነት እናንት ናችሁ ፡ እናንተ አብነት ካልሆናችሁ ማን አብነት ይሆንላችኋል ፣ እንድም ለሕዝቡ እናንተ አብነት ካልሆናችኋቸው ማን አብነት ይሆና ቸዋል ። ለሕዝቡ የምትረቧቸው የምትጠቅሟቸው የለም ። እንድም ለራሳችሁ የምታገኙት ረብሕ ጥቅም የለም ። ዘእንበለ ዘይገድፍዎ አፍአ ፣ ሕዝቡ ከልቡ ናቸው በአፍአ ያወጥዋችኋል ፣ ወይከይድዎ ። በልቡናቸው ይንቅፉችኋል እንጂ ። እንድም ሥላቤ ክመንግሥተ ሰማይ አፍአ ወደምትሆን ወደ ገሃነም ያወጧችኋል እንጂ ፤ ወይከይድዎ ፣ አጋንንትም መከራ ያጸኑባችኋል እንጂ ። በማደሪያቸው ሰብእ አላቸው ። እንድም በቋሙ ሰዎች ይጠቀጥቋችኋል ቅዱስ ጊዮርጊስ እንዳሰነሣው ፍቁራ እስነሥቶ ወዴት ነበርህ ቢለው ከኤጲስ ቆጶሳችሁ ላይ ነበርሁ ብሏል

፲፬ እንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ።

፲፬ አብነትነታቸው በብዙ ወገን ነውና ደገ መው ፤ የሰው አብነቱ እናንተ ናችሁ ።
ኢትክል ተኀብኦ ሀገር እንተ ተሐንጸት መልዕልተ ደብር ፣ ከተራራ ላይ የተሠራች መንደር መሰወር አይቻላትም ።

፲፭ ወኢየኃትው ማኅቶተ ከመ ያንብርዋ ታሕተ ከፊር ። ማር ፬ ፣ ፳፩ ፣ ሉቃ ፡ ፰ ፣ ፲፮ ።

፲፭ እንቅብ ቅርጫት ሊደፋባት መቅረዝ የሚ ያበራ የለም ። አላ ያነብርዋ ዲበ ተቅዋማ ወታበርህ ለኵሉ እለ ውስተ ቤት ከመቅረዝ ላይ አኑረዋት ከቤት ላሉ ሁሉ ታበራ ዘንድ ነው እንጂ ።

፲፮ ከማሁኬ ይብራህ ብርሃንክሙ በቅድመ ሰብእ ። ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።

፲፮ እንዲህም ሁሉ ሥራችሁ በሰው ፊት ይሁን ከመ ይርአዩ ምግባሪክሙ ሠናየ ወይሰብሕዎ ለአቡ ክሙ ዘበሰማያት ።

በጐ ሥራችሁን አይተው ሰማያዊ አባታችሁን ያመ ሰግኑት ዘንድ እንዲህ ያሉ የትሩፋት አበጋዝ ያሰኘ ማልን ብለው ፣ ሐተታ ፡ ምነው በሚያመጣው ጸሊ በጎቡእ ይል የለም ቢሉ አብነት የሚሆኑበትን ተገ ልጸው ይሠሩታል አብነት የማይሆኑበትን ተሰውረው ይሠሩታልና እንዲህ አለ ፤ እንድም በተራራ ላይ የታነጸች መንደር ልሰወር ብትል መሰወር እንዳይ ቻላት የተራራው ክፍታ እንዲገልጻት ። በመቅረዝ ላይ ያለች ፋና ልሰወር ብትል መሰወር እንዳይቻላት የመቅረዙ ክፍታ እንዲገልጻት ፤ እናንተም ሥራውን አብዝታችሁ ሥሩት ግድ በተአምራት ይገልጻችኋል ሲል ነው ። ደብር ተቅዋም እንድ ወገን ሀገር ማኅ ቶት እንድ ወገን ፣ ደብር ተቅዋም ሥጋ ሀገር ማኅቶት ነፍስ ፣ ከሥጋ ጋራ የተዋሐደች ነፍስ ሥራ ሠርታ ልትገለጽ ነው እንጂ ፣ ተሰውራ ልትቀር አይደለም እንድም ደብር ተቅዋም ሰውነት ሀገር ማኅቶት አእ ምሮ ጠባይዕ በሰውነት ያለ አእምሮ ጠባይዕ ሥራ ሠርቶ ሊገለጽ ነው እንጂ ተሰውሮ ሊቀር አይደለም እንድም ደብር ተቅዋም ሥጋ ሀገር ማኅቶት መለኮት ከሥጋ ጋራ የተዋሐደ መለኮት አስተምሮ ታምራት አድርጐ አምላክነቱን ሊገልጽ ነው እንጂ ፣ ተሰ ውሮ ሊቀር አይደለም ። እንድም ደብር ተቅዋም መስ ቀል ሀገር ማኅቶት ጌታ በመስቀል የተሰቀለ ጌታ ሙቶ ተነሥቶ አምላክነቱን ሊገልጽ ነው እንጂ ሙቶ ሊቀር አይደለም ፣ እንድም ደብር ተቅዋም አሪት ሀገር ማኅቶት ወንጌል በኦሪት ላይ የተሠራች ወንጌል ባደባባይ ተገልጻ ልትነገር ነው እንጂ ። ተሰውራ ልትቀር አይደለም ። እንድም ደብር ተቅ ዋም ሕዝቡ ሀገር ማኅቶት ኤጲስ ቆጶስ በሕዝቡ ላይ የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ካደባባይ ወጥቶ ጉባኤ ሰርቶ ሕዝቡን ሊያስተምር ነው እንጂ ፣ ባዳራሽ ገብቶ አልፍኝ ተከቶ ተሰውሮ ሲባላ ሲጠጣ ሊውል አይ ደለም

፲፯ ኢይምሰልክሙ ዘመጻእኩ እሥዓሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት ፣ ብፁዓን ብፁዓን እያለ ሲያስ ተምር ሰምተው ኦሪትን ነቢያትን እንጂ ሊያሳልፋ ቸው መጥቷል እንዲሉት ዐውቆ አመጣ ። እንዲሉ ትም ዐውቆ ማምጣት ልማድ ነው ። ትውልደ አራ ዊተ ምድር ቢላቸው አብርሃምን ያሀል አባት ሳለን ትውልደ አራዊተ ምድር ይለናል እንዲሉት ዐውቆ ኢይምሰልክሙ ዘታመሰጡ በብሂለ አብ ብነ አብ ርሃም እንዳለ ፣ ወኢትሁብ ለጻድቅከ ይርአይ ሙስና ሙስና ቢላቸው ይህንማ ዳዊት ለራሱ የተናገረው አይደለም እንዲሉት ዐውቆ ታበውሑነሁ እ.ስብእ ንንግርከሙ ክሡተ በእንተ ዳዊት ርእሰ አበው ከመሂ ሞተ ወተቀብረ ወኀቤነ ሀሎ መቃብሪሁ እስከ የም እንዳለ ፣ ከዚህም እንዲህ አለ ፤

፲፯ ኦሪትን ነቢያትን ላሳልፋቸው የመጣሁ እይምሰላችሁ ኢመጻእኩ ይላል ፡ ላሳልፋቸው አል መጣሁም ።

ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ እፈጽሞሙ ።

ፍጹማን ላደርጋቸው ነው እንጂ ፤ ኢትቅትልን በኢታምዕዕ ኢትፍቱን በሀርአያ ላጸናቸው ነው እንጂ ወፈጸመ ሕገርትዕ በሕገ ትሩፋት እንዲል ።

፲፰ አማን አማን እብለከሙ እስከ አመ የሐልፍ ሰማይ ወምድር የውጣ እንተ አሐቲ ኅርመታ ወአሐቲ ቅርጸታ ኢተሐልፍ እምኦሪት ወእምነቢያት እስከ ሶበ ኵሉ ይትገበር ወይከውን ። ሉቃ፡፲፮፡፲፯ ።

፲፰ ሰማይ ምድር እስኪያልፍ ይህ ሁሉ እስኪሆን ይህ ሁሉ እስኪደረግ ድረስ ሥርዓቷ ጽፈቷ አንዲት የምትሆን ኢትፍቱስ እንኳ ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ አታልፍም ብየ እንዳታልፍ በውነት እነግራችኋለሁ ዮድ ለአሌፍ ዐሥረኛ እንደ ሆነ ኢትፍቱም ለኢታምልክ ዐሥረኛ ናትና ። አንድም አሰራረዟ አቀራረጹዋ እንድ የምትሆን ዐሥርቱ ቃላት ሁሉ ሲያልፍ ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ እንዳታልፍ አታልፍም ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ፡ በሀገራቸው ፲ቱ ሲሉ የውጣ ይላሉ አንዲት ጭራ ናት ዕዝል ቅጽል የላትም ። በኛም ፲ አንዲት ጭራ ናት ዕዝል ቅጥል የላትም ። አንድም ለኛ ፊደል ዐሥረኛውት ነው፤መስቀላዊት ሕገ ክርስቶስ ወንጌል ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ ወደሰው ልቡና አትገባም ብየ እነግራችኋለሁ ። ወኀለፈት ሰንበት እንዲል ፡ አብራ ትነገራለች እንጂ ማለት ነው ፤ ውኅጣ የሚል አብነት ይገኛል ። የውጣ ማለት ነው ። በዳር ሮ ሎ ብሎ ይገኛል ፡ ሮ ቢል ከመንግሥተ ሮም የምትበልጥ ሎ ቢል ልዕልት የምትሆን ወንጌል ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ ወደሰው ልቡና አትገባም ብየ እንዳትገባ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፲፱ ዘኬ ፈትሐ አሐተ እምእላ ትእዛዛት እንተ ተሐጽጽ ወይሜህር ከመዝ ለሰብእ ሕጹጸ ይከውን በመንግሥተ ሰማያት ። ያዕ፡ ፪፡ ፲ ።

፲፱ ካ፲ቱ ቃላት አንዲቱ ታናሽ ናት ብሎ ለራሱ የሚሠራ ለሌላው የሚያስተምር ውፁእ ሲል ነው ከመንግሥተ ሰማያት የወጣ ይሆናል ፡ መኑ እብእ ለዘ እግዚአብሔር አሕጸጾ ወሐጽ መንፈቅ ወየሐጽጾሙ እመንግሥተ እቡሁ እንዲል ፤ ወዘሰ ይገብር ወይሜህር ከመዝ ለሰብእ ውእቱ ዐቢየ ይከውን በመንግሥተ ሰማያት፥ከዐሥርቱ ቃላት አንዲቱ ደግ ናት ብሎ ለራሱ የሚሠራ ለሌላው የሚያስተምር ግን ለመንግሥተ ሰማያት ባለቤት ይሆናል ። አንድም ይከውን ሕጹጸ ፡ እንደ ጨረቃ እንደ ንኡስ ኮከብ ይሆናል ፤ ይከውን ዐቢየ እንደ ፀሐይ እንደ ዐቢይ ኮከብ ይሆናል ።

፳ ናሁ እብለክሙ ከመ ለእመ ኢፈድፈደ ጽድቅክሙ እምጸሐፍት ወፈሪሳውያን ኢትበውኡ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፴፱ ።

፳ በቁሙ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ናቸው ብሎ ፡ ሥራችሁ ከጸሐፍት ከፈሪሳውያን ሥራ ካልበለጠ ኢያፈድፈድክሙ ጽዲቀ አብዝታችሁ ሥራ ካልሠራችሁ መንግሥተ ሰማያት አትገቡም ብየ እንዳትገቡ በውነት እነግራችኋለሁ ። እኒያም አልገቡ እናንተም አትገቡ ማለት ነው ። አንድም ደጋጎች እለ አብርሃም እለ ሙሴ እለ ዳዊት ናቸው ብሎ ሊቁ ወስዶታል ብሎ በሥራ መበላለጥ ከሌለ በክብርም መበላለጥ የለም ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ። ሥራው ምንድ ነው ቢሉ እፍቅሮ ጸላዕት ተዐፍሮ መልታሕት መንና ጥሪት ነው ። ይህንማ እነሱስ አድርገውት የለም ለእመ ርኢከ አድግ ፀላዒከ ዘኃየሎ ጾሩ ኢትትዓደዎ አላ አስተልዕል ምስሌሁ እንዲል ዘፀ ፳፫፡፭ ፡ አድርገውት የለም ቢሉ መጥዎተ ርእስ ነው ይህንስ አድርገውት የለም ሙሴ እምትጥስዮሙ ለእሉ ሕዝብከ ጠስየኒ እመጽሐፈ ሕይወትከ ብሏል ዘፀ ፴፪፡፲፮ ፡ ዳዊትስ ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ እንዘ ኖላዊሆሙ አነ ዘአበስኩ ፤ ዳዕሙ ለትረድ እዴከ ላዕሌየ ወላዕለ ቤተ እቡየ ብሎ የለም ቢሉ ፡ እኒያ ለዘመዶቻቸው ነው ፤ እናንተ ግን ለሁሉ አድርጉት ሲል እኒያ እስበውት ቀርቷል እናንተ ግን አድርጉት ሲል ነው ፡ ዳግመኛ ሕግ ሁኖ ስላልተጻፈ ተጽፎ የለም ቢሉ ገብሩ ተብሎ ተጽፏል እንጂ ግበሩ ተብሎ ተጽፏልን ፤ በሥራም ካልተበላለጣችሁ ማለቱስ እንደ ምነው ቢሉ ለእኒያ አብነት አልነበራቸውም ለኒህ ግን አብነት ጌታ አላቸውና ፡ እኒያ በልጅነት አልታደሉም እኒህ ግን በልጅነት ታድለዋልና ። ለኒያ አጋዥ አልነበራቸውም ለኒህ ግን አጋዥ ሥላሴ መላእክት መጻሕፍት መምራን አሏቸውና ።

፳፩ ሰማዕክሙ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ ኢትቅትል ነፍሰ ።

፳፩ ለቀደሙ ሰዎች ነፍስ አትግደል የተባለውን ዘጸ ፳፡፲፫ ዘከመ ተብህለ ሎሙ እንደተባለላቸው ዘይቤልዎሙ ያሏቸውን ዘከመ ይቤልዎሙ እንዳሏቸው ሰምታችኋል ።

ወዘሰ ቀተለ ረስሐ ውእቱ ለኵነኔ ።

ነፍስ የገደለ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል የተባለውን ሰምታችኋል ።

፳፪ ወአንሰ እብለክሙ ኵሉ ዘያምዕዕ እኅዋሁ በከንቱ ረስሐ ውእቱ ለኵነኔ ።

፳፪ እኔ ግን ወንድሙን በከንቱ ያሳዘነ ሁሉ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል ብየ እነግራችኋለሁ ፤ ሐተታ ኦሪትንስ ወንጌልንስ የሠራ እሱ አይደለም እኔ ግን

ማለቱ ስለምን ቢሉ ጌታ ሁን እንዳሻህ ሁን እንዲሉ ይህስ በጌታ የለበትም ብሎ አሪትን በሙሴ በኢያሱ አድሮ ሠርቷታል ወንጌልን ግን እሱ ሰው ሁኖ ሠርቷታልና ፤ አንድም ለቀደሙ ሰዎች እንዲህ ብየ ነበር ዛሬ ግን እንዲህ እልሁ ። አንድም አሚሃኒ ዮምኒ ያን ጊዜ እንዲህ ብየ ነበር ዛሬም እንዲህ እልኩ ። በከንቱ እለ ቦ መዓት ዘበርትዕ እንዲል ፤ የሚገባ ቁጣ አለና ሕፃናት ያል ተማሩትን እንዲማሩ የተማሩትን እንዳይገድፉ መናፍቃን እንዳይሠለጥኑ ሃይማኖት እንዳይጠፋ ክህደት እንዳይሰፋ ፣ አንድም በከንቱ ያለውን መፍቀርያን መዓት የጨመሩትን ነው በሐጌ መጽሐፍ ፳፫ ፣ ዝወርቅ ወዝ ብሩር ዘዚአየ ባለው መፍቀርያን ብሩር ወለዘፈቀድኩ እሁቦ ባለው እንደጨመሩበት ወዘሂ ይቤሎ ኅሡር ዘጸርቅ ረሰሐ ።

ወንድሙን ጨርቅ ለባሽ እባተ ታናሽ ብሎ የሰደበ በደለ ፤
ወይትኴነን በዐውድ
በዐደባባይ ይፈረድበታል ።
ወዘሂ ይቤሎ ለእኁሁ ዓብድ ረሰሐ ውእቱ ።
ወንድሙን ዲዳ ደንቆሮ ያለው እሱ በደለ ።
ወይትኴነን በእሳተ ገሃነም ።

በእሳተ ገሃነም ይፈረድበታል ሐተታ ወንድሙን ጨርቅ ለባሽ እባተ ታናሽ ቢለው ባደባባይ ፤ ድዳ ደንቆሮ ቢለው በገሃነም ይፈረድበታል አለ ምነው ቢሉ ፣ ከተፈጥሮተ ሥጋ ተፈጥሮተ ነፍስ እንዲበልጥ ከስድቡም ስድቧ ይበልጣልና ፣ ከፍዳውም ፍዳውን አበለጠ ፤ አንድም በዓውድ ገሃነም በገሃነም ዓውድ ያዕነው።በአክብርዎ ፍርሀዎ በፍርሀዎ አክብርዎ እን ዳለ ። ይህንም ሊቁ ዘለ ፀረፈ ላዕለ ሰብእ ጸረፈኬ ላዕለ እግዚአብሔር ብሎ ወስዶታል ። መጽሐፉን አይቶ መንቀፍ ጸሐፊውን ሕንጻውን አይቶ መኝቀፍ ሐናጺውን መኝቀፍ እንደሆነ ፍጥረቱንም አይቶ መንቀፍ እግዚአብሔርን መንቀፍ ነውና ።

፳፫ ወእምከመኬ ታብውእ መባዐከ ውስተ ምሥዋዕ ወበህየ ተዘከርከ ከመ ቦ እኁከ ዘተኃየሰከ ።

፳፫ መባህን ለቤተ እግዚአብሔር በምትሰጥ በት ጊዜ አንተ ወንድምህን የነቀፍህበት ፣ ዘተኃየ ሰከ እሱ አንተን የነቀፈበት ነገር እንዳለ ብታሰብ ።

፳፬ ኅድግ ህየ መባዐከ ቅድመ ምሥዋዕ ።

፳፬ መባውን ከደጇ ሰላም እኑረህ ወሑር ቅድመ ተኳነን ምስለ እኁከ ።

እስቀድሙህ ከወንድምህ ተወቃቅሰህ ታረቅ ።
ወእምዝ ገቢእከ አብእ መባዐከ፣ ከዚህ በኋላ ተመል ስህ መባህን ስጥ ። ሰጥቶ ቢሄድ መባው እንኳን የገ ባልኝ እንጂ ብሎ ዕርቁ በቀረ ነበርና ፤ ይዞ ወደ ቤቱ ተመልሶ ቢሆን ዕርቁም መባውም በቀረ ነበርና ልብ እንዲቀረው ከእዳሪ እኑራለሁ ብሎ ፈጥኖ ታርቆ እንዲመለስ እንዲህ አለ አንድም ወእምከመኬ ብለህ መልስ ጸሎት በምትጸልይበት ጊዜ የነቀፈህ ወንድ ምህ የነቀፍከው ወንድምህ እንዳለ ብታስብ ጸሎቱን ትተህ ሂድ አስቀድመህ ከወንድምህ ተወቃቅሰህ ታረቅ ከዚህ በኋላ ተመልሰህ ጸሎትህን ጸልይ ። በቂም በበቀል ሁኖ የጸለዩት አይረባም አይጠቅም ምና እስመ ዘያነብር ቂመ ውስተ ልቡ ኢውክፍት ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር ጸሎቱ ለመስተቀይም ከመ ዘርዕ ዘወድቀ ማእከለ አስዋክ እንዲል ።

፳፭ ኩን ጠቢበ ለዕድውከ ፍጡነ እንዘ ሀሎከ ምስሌሁ ውስተ ፍኖት ።

፳፭ በመንገድ ከሱ ጋራ ሳለህ በባላጋራህ ፈጥ ነህ ዕወቅበት ታረቅ በፍኖት ብሎ በሉቃስ ያቀና ዋል ።

ከመ ኢይመጡከ ዕድውከ ለመኰንን
ባላጋራህ ለዳኛ አሳልፎ እንዳይሰጥህ ።
ወመኰንን ይሚጥወከ ለወዓሊሁ ።
ዳኛውም አሳልፎ ለሎሌው ይሰጥሃል ።
ወወአሊሁ ይሞቅሐከ ።
ሎሌውም ያግዝሃል ።

፳፮ አማን እብለከ ከመ ኢትወፅአ እምህየ እስከ ሶበ ትሜልጥ ደኃሪተ ገመለ ዘሳዕሌከ ።

፳፮ ሌላው ገንዘብህስ ይቅርና ሰንኪቶ የምት ባል ቀለበትህን እስከመስጠት ደርሰህ ፤ አንድም ገመሰ ደኃሪት ይላል ፤ የታናሽ ጣትህን ቀለበት እስከ መስጠት ደርሰህ ከግዞት ቤት አትወጣም ብየ እንዳ ትወጣ በውነት እነግርሃለሁ ። አንድም ኩን ጠቢበ ብለህ መልስ በዚህ ዓለም ሳለህ በባለጋራህ በዲያብ ሎስ ዕወቅበት ። ይህን ዓለም ፍኖት አለው በመን ገድ አንዱ ሲያልፍ አንዱ ሲተርፍ እንደሆነ በዚህም ዓለም አንዱ ሲያልፍ አንዱ ሲተርፍ ነውና ። ባለ ጋራህ ዲያብሎስ ለጌታ አሳልፎ እንዳይሰጥህ ። ጌታም አሳልፎ ለዲያብሎስ ይሰጥሃል ። ዲያብሎስ ያግዝሃል ። ወዓሊሁ አለ የግድ ነው የፈቃድ አይደ ለም ። ሥራ ሠርተህ ያገኘኸው ጸጋ ክብር ይቅርና በርባቀን ያገኘኸውን ልጅነት እስከ ማጣት ደርሰህ ከገሃነም አትወጣም ብየ እንዳትወጣ በውነት እነግ ርሃለሁ ። አንድም ፣ በዚህ ዓለም ሳለህ በባለጋ ራህ በፈቃደ ሥጋህ ፈጥነህ ዕወቅበት ። ባላጋራህ ፈቃደ ሥጋ አስፈርዶ ለጌታ እንዳይሰጥህ ። ጌታም አሳልፎ ለዲያብሎስ ይሰጥሃል ፤ ዲያብሎስ ያግዝሃል አማን እብለከ ። በነቢብ በገቢር በሠራኸው ኃጢ አት ቀርቶ በሐልዮ በሠራኸው ኃጢአት ተፈርዶብህ ከገሃነመ እሳት አትወጣም ብየ እንዳትወጣ በውነት እነግርሃለሁ ። ከሐልዮ ኃጢአት የሚነጻ አለን ቢሉ

የሚየሲዝ ሐልዮ የሚያሲዝ ሐልዮ አለ ። የሚያሲዝ ሐልዮ እስርቃለሁ እቀማለሁ ብሎ ሂዶ ሰው ነቅቶበት ውሻ ጩሆበት አጥር ጠንቶበት ቢመለስ ያሲዛል ፤ የማያሲዝ ሐልዮ እስርቃለሁ እቀማለሁ ብሎ ይሄዳል ከመንገድ ሲደርስ ፈጣሪዩ ቢፈርድብኝስ ብሎ የተመለሰ እንደሆነ ይህ አያሲዝም ። አንድም ሁሉም ያሲዛል ለዚህ ቅሉ ጥቂት ቀኖና ያሻዋል በሰይጣን ጻር ተወግቷልና ፣ ሁለት ሰዎች ከስልፍ ይገባሉ ሁለቱ ሁሉ ተወግተው ይመለሳሉ አንዱ ይሞታል አንዱ ይድናል ከዳነው ላይ እትራት ይጠፋልን ፤ ይህም በአቡነ እንጦንስ ታውቋል በሚሞቱበት ጊዜ መላእክተ ጽልመት ቀረቡ መላእክተ ብርሃን መጥተው ከዚህ ሰው ምን አላችሁ አሏቸው ፤ ምነው ያሰ የሐልዮው አሏቸው ከቆብ በኋላ ነው ከቆብ በፊት አሏቸው ከቆብ በፊት ነው እንጂ ከቆብ በኋላማ በእንጦንስ ምን ተገኝቶበት አሉ ። ያማ በቆብ ታርቆበት የለም ወግዱ ብለዋቸዋል ።

፳፯ ሰማዕክሙ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ ኢትዘምው ። ዘፀ ፳ ፣ ፲፬ ።

፳፯ ለቀደሙት ሰዎች አትስስኑ የተባለውን ሰምታችኋል ።

፳፰ ወአንሰ እብለክሙ ኵሉ ዘርእያ ለብእሲት ወፈተዋ ወድአ ዘመወ ባቲ በልቡ ።

፳፰ እኔ ግን ቤትን ያየ ሁሉ ፈጽሞ በደለ ብየ እነግራችኋለሁ ርእይን መከልከሉ ነው ቢሉ አዎን አርቆ ማጠር ነው ፤ አንድም ፈተዋ ያለውን ይሻል አይቶ ባገኟት ቢል ።

፳፱ እመኒ ዓይንከ ዘየማን ታስሕተከ ምልሖ ወግድፋ እምላዕሌከ ማር ፱ ፣ ፵፯ ፤ ማቴ ፲፰ ፣ ፱ ።

፳፱ ቀኝ ዓይንህ ምክንያተ ስሕተት ብትሆን ብህ ከንተ አውጥተህ ጣላት ።

እስመ ይኄይሰከ ነቋረከ ትባእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት እምትባእ ውስተ እሳተ ገሃነም ምስለ ከ፪ ሆን አዕይንቲከ ፣ ዛሬ ሁለት ዓይን ኑሮህ ኋላ ገሃነም ከምትገባ በዚህ ዓለም ሳለህ ከሁለት ዓይንህ አንዱ ጠፍቶ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፤ ይህን ያደረጉ ብዙ ናቸው ከዚያው ግን ስምኦን ስፋዬ እማዕን ፤ አንዲት ሴት ወይዘር መጥታ ጫማ ስፋልኝ አለችው ስፍቶ ሰጣት እየተመላለሰች አስችገረችው ጫማውን ነው ስፍቻ ሰጥቻሻለሁ ምን ያመላልስሻል አላት ፣ ይህ ሁሉ ምክንያት ነው አንተን ብወድህ ነው አለችው በምን ነገር አላት ፣ መልክ መልካም ነህና አለችው ምኔ መልካም ነው ቢላት ሁለንተናህ መልካም ነው ይልቁንም በዓይንህ ይጸናብኛል አለችው ትወጅዋለሽ አላት አዎን አለችው ። ይህማ ምን ቁም ነገር አለው ውኃ አይደለም ብሎ በያዘው መንጉል አውጥቶ ሰጥቷታል።

፴ ወእመኒ እዴከ ዘየማን ታስሕተከ ምትራ ወግድፋ እምላዕሌከ ።

፴ ቀኝ እጅህ ምክንያተ ስሕተት ብትሆንብህ ቁርጠህ ጣላት ። እስመ ይኄይሰከ ይታጐል አሐዱ አምአባልከ እምዙሉ ሥጋከ ይትወደይ ውስተ እሳተ ገሃነም ።

በዚህ ዓለም ከሕዋሳትህ አንዱ ሳይጐል ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትወርድ በዚህ ዓለም ከሕዋሳትህ አንዱ ጎድሎ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ። ይህን ያደረጉ ብዙ ናቸው ። ከዚያው ግን አባስ ካህን ሮሜ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሀገረ እንጾኪያ ፤ አባስ ካህን ሮሜ በተአምረ ማርያም ታውቋል አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘአንጾኪያ ቀድሞ አረማዊ ነበረ ኋላ አምኖ ተጠምቆ ተምሮ ተሾሟል በሀገራቸው የተሾመው ፯ ቀን ቀድሶ ያቈርባል በዚያ ልማድ በመስቀል እየባረከ ሲዞር ቀድሞ በአረማዊነት ሳለ በግብር የምታውቀው ቤት መለያ ይሁነኝ ብላ እጁን ነክሰችው ጦር ተነሣበት ከዚህ ሁሉ ያደረሰችኝ ይህች እጅ አይደለችም ብሎ ከዕቃ ቤት ገብቶ እጁን ቆርጦ ጣላት ፣ አባታችን ገብተህ ቀድስልን አሉት አይቻለኝም አላቸው ። ሁለተኛ ገብተህ ቀድስ አሉት አይቻለኝም አላቸው ፣ ይህ ሰው ወደ ቀደሙ ግብሩ ተመለሰን ብለዋል ወደ እመቤታችን አመለከተ እድ ብርህት ቀጠለችለት ገብቶ ሲቀድስ የእጁ ብርሃን እየበዘበዘ የማያሳያቸው ሆነ ወጥተው አባታችን ነገሩ ምንድነው ግለጥልን አሉት ምንጣፏን ግለጡት አላቸው ቢገልጡት ወድቃ አገኙዋት ይህች የኔ እጅ ናት ይህች እመቤታችን የሰጠችኝ ናት ብሏቸዋል ።

ወእመኒ እግርከ ዘየማን ታስሕተከ ምትራ ወግድፋ እምላዕሌከ ።

ቀኝ እግርህ ምክንያተ ስሕተት ብትሆንብህ ቆርጠህ ጣላት ፤ እስመ ይኄይሰከ ይትኃጐል ፩ዱ እምአባልከ እምዙሉ ሥጋከ ይትወደይ ውስተ እሳተ ገሃነም በዚህ ዓለም ከሕዋሳትህ አንዱ ሳይጎድል ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትወርድ፤በዚህ ዓለም ከሕዋሳትህ አንዱ ጐድሎ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ። ይህን ያደረጉ ብዙ ናቸው ከዚያው ግን አባ መርትያኖስ፡በዓቱ ከመንደር አጠገብ ነው ከበረሃ ውሎ ወደማታ ሲመለስ ዘማት ተሰብስበው አይተው ይህ መነኮስ ኃያል ጽኑዕ ነው የሚያስተው የለም አሉ ፤ አንዲቱ እኔ ባስተውስ ባታስችውስ ተባብለው ተወራርደዋል ፤ አሁን በጊዜ የሄድኩ እንደሆን አይቀበለኝም ብላ ሲመሽ ሒዳ እጅ ጸፋች ፤ ወጥቶ ማነሽ አላት ከሩቅ አገር የመጣሁ የእግዚአብሔር እንግዳ ነኝ የምጠጋበት አጥቸ አውሬ ይጣላኛል ወምበዴ ይቀጠቅጠኛል ብየ ቁሚያለሁ አለችው አዑም ባስገባት ጻር ይነሣብኛል አይሆንም ብላት

ነግደ ኮንኩ ወኢተወከፍክሙኒ ያለው ይፈርስብኛል እያለ ያወጣ ያወርድ ጀመረ ። ነግደ ኮንኩ ወኢተወከፍክሙኒ ያለውስ ቢፈርስብኝ ጡሩን እታገሥዋለሁ ብሎ እሳቱን እንድዶላት እሱ እልፍ ብሎ ጸሎቱን ያዘ እሷም የምትቀባውን ትቀባ የምታጤሰውን ታጤስ ጀመር ። መዓዛው ቢያስቸግረው እግሩን ከእሳቱ ማገዶው የሷን መዓዛ እስኪያጠፋው እስኪለውጠው ፤ ምትሬ ያለው ለዚህ ይመቻል ፤ እሷም አባቴ አላበጀሁም ብላ ንስሐ ገብታለች እንደም ገልጣ እንተኛ አለችው እንተኛማ ካልሽ ከእሳቱ ላይ እንተኛ አላት ይህማ ይፈጀን የለም አለችው የዚህን ዓለም እሳት ያልቻልነው የወዲያኛውንማ ዓለም እሳት እንደምን እንችለዋለን አላት አባቴ አላበጀሁም ማረኝ ብላ ንስሐ ገብታለች እሱም አመንኵሷት በእቴን ለቆላትሂዷል እንድም ዓይን የተባለች ሚስት ናት። ከዓይን የሚሰወር እንደሌለ ከሚስትም የሚሰወር የለምና ፤ ሚስትህ ያልሆነ ሥራ ላሠራህ ብትል ፈቃዷን አፍርስባት ዛሬ በዚህ ዓለም የሚስትህን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትገባ፥ በዚህ ዓለም የሚስትህን ፈቃድ አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፤ እጅ የተባሉ ልጆች ናቸው ወድቆ ይነሡ በእጅ ዜግቶ ይከብሩ በልጅ እንዲሉ ። ልጆችህ ያልሆነ ሥራ እና ሠራህ ቢሉ ፈቃዳቸውን አፍርስባቸው ፤ በዚህ ዓለም የልጆችህን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትወርድ፤ በዚህ ዓለም የልጆችህን ፈቃድ አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና እግር የተባሉ ቤተሰብእ ናቸው ቤተሰቦችህ ምክንያተ ስሕተት ሁነው ያልሆነ ሥራ እና ሠራህ ቢሉ ፈቃዳቸውን አፍርስባቸው ፤ በዚህ ዓለም የእሳቸውን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም እሳት ከምትገባ ፤ በዚህ ዓለም ፈቃዳቸውን አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፤ እንድም እንዳይንህ እንደ እጅህ እንደ እግርህ የምትወደው ወዳጅህ ያልሆነ ሥራ አሠራሃለሁ ቢልህ ፈቃዱን አፍርስበት በዚህ ዓለም የሱን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትገባ ። በዚህ ዓለም የሱን ፈቃድ አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፤ እንድም ምድራውያን ነገሥታት ዓይን በፍላት እጅ እግር በሰለት ፤ እንዲቀጹ ሌዋውያን ካህናት ዓይንን በእንቃዕድዎ እጅን በሰፊህ ፤ እግርን በቀዊም ፡ ሠርተው ቀጽተው እንዲኖሩ ፤ አንተም ዓይንህን በእንቃዕድዎ እጅህን በሰፊህ እግርህን በቀዊም ሥራ ቅጻ ።

፴፩ ሰማዕክሙ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ ኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ ይጽሐፍ ላቲ መጽሐፈ ሕዳጋታ ወየሀባ ። ዘዳ ፳፬፥ ፩ ማቴ ፲፱፥፯፥፱ ማር ፲፥፬፥፲፪ ሉቃ ፲፮ ፥ ፲፰ ፥ ፩ ቆሮ ፯ ፥ ፲ ።

፴፩ ከናንት አስቀድሞ ለነበሩ ሰዎች ሚስቱን የሚፈታ ሰው ሁሉ የምትፈታበትን ነውር የሚናገር ደብዳቤ ጽፎ ሰጥቶ ይፍታት የተባለላቸውን ሰምታችኋል ፤ እንዳለፈው በል ።

፴፪ አንሰኬ እብለክሙ ኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ ዘእንበለ ትዝሙ በላዕሌሁ ለሊሁ ረሰያ ዘማ

፴፪ እኔ ግን ሳትሰስንበት ሰነፈች ደረቀች ብሎ ሚስቱን የፈታ ሰው ሁሉ ዘማ አሰኛት ብየ እነግራችኋለሁ ።

ወዘሂ አውሰበ ኅድግተ ዘመወ በነውር የተፈታችውን ያገባ በደለ ፤ በምን ያውቀዋል ቢሉ አቡን ፅጨጌ ይፍቱኝ ባለማለቷ ፤ ኋላ እንደምን ትሁን ቢሉ የፍርድ መጽሐፍ በጉጉዓ ብሎ ወስዶታል ። ንስሐ መግባቷን መምህረ ንስሐዋ ጉረቤቶቿ መስክረውላት ታግባ ብሏል ። እንድም ሰማዕክሙ ብለህ መልስ ። አሪትን የሚተው ሰው ሁሉ ወንጌልን ተከቶ ይተው የወንጌልን ሥራ ሳይሠራ ግን አሪትን የተወ ሰው ወንጌልን ኃላፊት ሕግ አደረጋት ። ከተዋትም በኋላ ወደ አሪት ቢመለስ በደለ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል እንድም መልስ ይህን ዓለም የሚተው ሰው ሁሉ መንግሥተ ሰማያትን ተከቶ ይተው ። የምናኔ ሥራ ይሥራ ። ወእንሰ እብለክሙ ፤ የምናኔ ሥራ ሳይሠራ ይህን ዓለም ተውሁ የሚል ሰው ግን መንግሥተ ሰማያትን ኃላፊት ርስት አደረጋት ። ከመነነም በኋላ ወደኋላም ቢመለስ በደለ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል።

፴፫ ወካዕበ ሰማዕክሙ ዘተብህለ ለቀደምትበሙ ኢትምሐሉ በሐሰት ፤ ወባሕቱ አግብኡ መሐላክሙ ለእግዚአብሔር ። ዘሌዋ ፲፱፥፲፪ ዘፀ ፳፥፯ ዘዳ ፳፫፥፳፩ ያዕ ፭፥፲፪ ፤

፴፫ ለቀደሙ ሰዎች በእውነት እንጂ በሐሰት በስመ እግዚአብሔር እንጂ በስመ ጣዖት ዳኛ ፈርዶባችሁ ባለጋራ አውርዶላችሁ እንጂ ዳኛ ሳይፈርድባችሁ ባለጋራ ሳያወርድላችሁ አትማሉ ያሏቸውን ሰምታችኋል ።

፴፬ ወአንሰ እብለክሙ ኢትምሐሉ ግሙራ ።

፴፬ እኔ ግን ፈጽማችሁ አትማሉ እላችኋለሁ ።
ኢበሰማይ ።
በሰማይም ሁኖ ከሰማይ የመጣ መቅሠፍት አይላተን ሰማይ ተንዶ ይጫነን እያሉ ይምላሉና ፤ እስመ መንበሩ ለእግዚአብሔር ውእቱ ።
የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና ።
ወኢበምድር ።

በምድርም ሁኖ ምድር ይከዳን ምድር ተከፍቶ ይዋጠን እያሉ ይምላሉና ።
እስመ መከየደ እገሪሁ ይእቲ ፤
መመላለሻው ናትና ።

፴፭ ወኢበኢየሩሳሌም ፤

፴፭ በኢየሩሳሌምም ሁኖ ከበረከተ ርስት እያሳተፈን ከምድረ ርስት ያወጣን እያሉ ይምላሉና ።
እስመ ሀገሩ ይእቲ ለንጉሥ ዓቢይ ።
የደግ ንጉሥ የእግዚአብሐር የመመለኪያው አገር ናትና ።

፴፮ ወኢበርእስክሙ ኢትምሐሉ ፤

፴፮ በራሳችሁም እትማሉ እንዲህ ያድርገን እያሉ ይምላሉና ።
ወኢበስእርተ ርእስክሙ ፤
በራሳችሁ ጸጉር አትማሉ ፤ እንደ ራሳችን ጸጉር ያጥቁረን የራሳችንን ጸጉር ያህል አምራ መጥቶ ይብላን እያሉ ይምላሉና ።
እስመ ኢትክሉ አሐተ እምስእርተ ርእስክሙ ኢአጸዕድዎ ወኢአጽልሞ ።
ከራሳችሁ ጸጉር አንዱን ነጩን ጥቁር ጥቁሩን ነጭ ማድረግ አይቻላችሁምና ።

፴፯ ወይኩን ባሕቱ ነገርክሙ እመሂ እወ እወ ወእመሂ አልቦ አልቦ ። ያዕ ፭ ፥ ፲፪

፴፯ ነገራችሁ እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት ይሁን እንጂ ፤ ሐቲታ እወ ቢለው ያምንለታልን ቢሉ ይመንለት ወንጌል መሠረቷ ለሁሉ ነው እንጂ ላንድ ብቻ ነውን ይላሉ ባያምንለትስ ቢሉ ሙሐላውን በገንዘብ ያስቀረው ገንዘብ ባይኖረውሳ ቢሉ ይማል ዕዳው ባማይው ይሆናል እንጂ በማዩ አይሆንምና ወለእመ ኢተክህለ ይከውን ጌጋይ ላዕለ ዘአምሐሎ እንዲል ፤ ሐዋርያ ጳውሎስ ወመሐላ ለቅሥት የሐልቅ በመሐላ ይላል ፤ ከዚህ ጌታ ኢትምሐሉ አለ እንደምነው አይማላም ቢሉ አይማላም ። ሐዋርያ የርትዑን ጌታ የትሩፋቱን ተናገረ እንድም ሁሉም ርትዕ ነው ። ሐዋርያ ዳኛ ፈርዶባችሁ ባላጋራ አውርዶላችሁ ማሉ ሲል ነው ። ጌታ ዳኛ ሳይፈርድባችሁ አትማሉ ሲል ነውና እንድም ኢበሰማይ ብለህ መልስ በመለኮት አትማሉ ባሕርዩ ነውና ፤ ወኢበምድር በትስብእት አትማሉ ባሕርዩ ነው ። ወኢበ ኢየሩሳሌም ፤ በሥጋው በደሙ አትማሉ ባሕርዩ ነውና ፤ ወኢበርእስክሙ በክርስቶስ አትማሉ ፤ ንሕነ አባል ወውእቱ ርእስ እንዲል ፤ ወኢበስእርተ ርእስክሙ ፤ በጻድቃን በሰማዕታት አትማሉ ፤ እስመ ኢትክሉ ከጻድቃን ከሰማዕታት አንዱን ኃጥእ ጻድቅ ጻድቁን ኃጥእ ማድረግ አይቻላችሁምና ፤ ወፈድፋደሰ እምእሉ እምእኩይ ውእቱ ፤
ከእወና ከአልቦ የወጣ ግን ከሰይጣን የተገኘ ነው

፴፰ ሰማዕክሙ ዘተብህለ ዓይን ቤዛ ዓይን ወሥን ቤዛ ሥን ። ዘፀ ፡ ፳፩ ፡ ፳፬ ። ዘሌ ፡ ፳፬ ፡ ፳ ፤ ዘዳ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ።

፴፰ ዓይን ቢጠፋ ዓይን ይጥፋ ጥርስ ቢሰበር ጥርስ ይሰበር የተባለውን ሰምታችኋል ፤ ቢሆንቱ ለሚመጣው ለሌላው ነው ።

፴፱ ወአንሰ እብለክሙ ኢትትቃወምዎ ለእኩይ በእኩይ ። ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፱ ። ፩ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፯ ።

፴፱ እኔ ግን ክፉውን ሰው በክፉ ነገር ድል አትንሱት ክፉን ግብር በክፉ ግብር አታጥፉት እላችኋለሁ ። ወኀበዘሂ ጸፍዓከ መልታሕቴከ እንተ የማን ሚጥ ሎቱ ካልዕታሂ ፤
ቀኝ ፊትህን ቢመታህ ግራ ፊትህን አዙረህ ስጠው ፈቃደ ሥጋህን ተው ቢልህ ፈቃደ ነፍስህን ተውለት

፵ ወለዘሂ ይፈቅድ ይተዓገልከ መልበስከ ኅድግ ሎቱ ክዳነከኒ

፵ መጐናጠፊያህን ሊቀማህ ቢወድ ቀሚስህን ደርብለት ። ታሪክ እንዳንድ ባሕታዊ ወምበዶች እንግዶች መስለው መጡ እግራቸውን አጥቦ አብልቶ አጠጥቶ አሳደራቸው ሌት ተነሥተው እሱን አስረው መብራት አብርተው ያለ ገንዘቡን ይዘው ሄዱ ከሄዱ በኋላ መብራት አብርቶ ቢያይ ሁለት ድሪም የምታወጣ ጸምር አገኘ ይህችም ላንድ ጉዳይ ትሆናችኋለች ብሎ ተከትሎ ወስዶ ሰጣቸው ይህ ሰው እንዲህ ማድረጉ ከዚህ የበለጠ ዋጋ እንዳለ ቢያውቅ እንጂ ነው ብለው ተመልሰው ንስሐ ገብተው የሚኖሩ ሁነዋል ። እንድም አፍአዊ ግብርህን ሊያስተውህ ቢወድ ውሣጣዊ ግብርህን ተውለት

፵፩ ወለዘሂ አበጠከ እሐደ ምዕራፈ ሖር ምስሌሁ ፪ተ ።

፵፩ ትብትብ አሸክሞ አንድ ምዕራፍ ቢወስድህ ይህማ የግድ አይደለምን ብለህ የፈቃድ ሁለት ምዕራፍ ተሸክመህ ውሰድለት መምህረ ንስሐህ አንድ ሱባዔ ቀኖና ቢሰጥህ ይህስ ተስማምቶኛል ጨምርልኝ ። ብለህ ከሱ አስፈቅደህ ሁለት ሱባዔ ጹም ፤

፵፪ ወለኵሉ ዘሰአለከ ሀቦ ። ዘዳ ፲፭ ፡ ፯፡፰

፵፪ ለለመነህ ሁሉ ስጠው ፤
ወለዘይፈቅድ ይትለቃሕ እምኔከ ኢትክልኦ ።
ካንተ ሊበደር የሚወደውን አትከልክለው እንደ ዮሐንስ መሐሪ መጥተው አበድረን ሲሉት መክፈቻውን ሰጥቶ ወደ ዕቃ ቤቱ ይሰዳቸዋል የሚበቃቸውን ያህል ይዘው ይሔዳሉ አምጥተው የሰጡት እንደሆነ ይቀበላል ባይሰጡትም ግድ የለውም ነበር ።

፵፫ ሰማዕክሙ ዘከመ ተብህለ ለቀደምትክሙ አፍቅር ቢጸከ ወጽላእ ጸላኢከ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፲፰ ።

፵፫ ከናንተ አስቀድሞ ለነበሩ ሰዎች ወዳጅህን ውደድ ጠላትህን ጥላ ያላቸውን ሰምታችኋል ።

አፍቅር ቢጸክ ይሁን ጽላእ ጸላኢክ የሚል በኦሪት ወዴት አለ ቢሉ ባጸሬው ተናገረ ወጻጅሀን ውደድ ማለት ጠላትህን ጥላ ማለት ነውና ፤ አንድም ተጸረርዎሙ ለሚደናውያን ኢትርስዮ ለአማሌቅ ያለውን ለውጦ አነበበው ።

፵፬ ወአንሰ እብለክሙ አፍቅሩ ጸላእተክሙ ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፯ ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፳ ግብ ሐዋ ፡ ፯ ፡ ፶፱ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ።

፵፬ እኔ ግን ጸላታችሁን ውደዱ እላችኋለሁ ፤ ወባርክዎሙ ለእለ ይሰድዱክሙ ከሀገራችሁ አሰወጥተው የሚሰዷችሁን መርቋቸው ከቦታችሁ ከሀገራችሁ አያናውጣችሁ ከመንግሥተ ሰማያት አያውጣችሁ እያላችሁ ። ሠናየ ግበሩ ለእለ ይጸረሩክሙ ለሚጠሏችሁ በጎ ሥራ ሥሩላቸው ።

ወጸልዩ በእንተ እለ ይትዔገሉክሙ ።

ሥቃይ ለሚያጸኑባችሁ ጸልዩላቸው አንዳንድ ምእመን ዘመነ ዓላውያን ሁኖ አንድ ዓላዊ መከራ ያጸናበታል ጌታዬ ምረረ ገሃነምን ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን ባያውቅ እንጂ ነው እንዲያውቅ አድርገው እያለ ይጸልይለታል ኋላ ዘመነ ዓላውያን አልፎ ዘመነ ክርስቲያን ሆነ ያ ክርስቲያን ዛሬ ቢያገኘኝ እንደምን ባደረገኝ ነበር አለ ። እሱስ ቀድሞም እንዲህ እያለ ይጸልይልህ ነበር አሉት እኒህ ክርስቲያን ምግባራቸው የቀና መሆኑ ሃይማኖታቸው እንጂ የቀና ቢሆን ነው ብሎ ተመልሶ አምኗል፣ ተጠምቋ ።

፵፭ ከመ ትኩኑ ውሉዶ ለአቡክሙ ዘበሰማያት

፵፭ የሰማያዊ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ዘንድ ማለት ሰማያዊ አባታችሁን ትመስሉ ዘንድ ። እስመ ውእቱ ያሠርቅ ፀሐየ ላዕለ ኄራን ወእኩያን ፀሐይን ለበጐዎችም ለክፉዎችም ያወጣልና ። ወያዘንም ዝናመ ላዕለ ጻድቃን ወኃጥአን ። ዝናምን ለጻድቃንም ለኃጥአንም ያዘንማልና ። ፀሐይ ሥጋው ደሙ ዝናም ወንጌል ነው በእንቢተኝነታቸው ይቅርባቸው እንጂ ሥጋው ደሙ ወንጌል የተሠራ ለሁሉ ነውና ።

፵፮ ወእመሰ ዘአፍቀረክሙ ታፈቅሩ ምንትኑ ዕሤትክሙ ።

፵፮ የወደዳችሁንማ ብቻ ብትወዱ ዋጋችሁ ምንድነው ።

አኮሁ መጸብሐንሂ ከማሁ ይገብሩ ።

የወደዳቸውንማ ብቻ መውደድ አጣሮችስ ያደርጉት የለምን ይህንስ አጣሮችም ያደርጉታል ባንዱ አገር ያሉ አጣሮች ባንዱ አገር ካሉ ጋራ ይጠቃቀማሉና ።

፵፯ ወእመሂ ተአምኁክሙ ቢጸክሙ ባሕቲቶ ምንት እንከ ፍድፋዴ ዝበርክሙ ።

፵፯ ወንድማችሁን ብቻ የምታከብሩ ከሆነ አብልጣችሁ ምን ትሩፋት ሠራችሁ ፣ ምንት ፍድፋዴ ዘገበርክሙ ፤ የሠራችሁት ትሩፋት ምንድነው ፤ አኮኑ አሕዛብኒ ከማሁ ይገብሩ ወንድማቸውንማ ብቻ መውደድ አሕዛብስ ያደርጉት የለም ይህንስ አሕዛብም ያደርጉታል ።

፵፰ አንትሙሰ ኩኑ ፍጹማነ ከመ አቡክሙ ሰማያዊ ፍጹም ውእቱ ።

፵፰ እናንተስ ሰማያዊ አባታችሁ ሁሉን አስተካክሎ በመውደድ ፍጹም እንደሆነ ሁሉን አስተካክላችሁ በመውደድ ፍጹማን ሁኑ ።

በእንተ ጾም ወጸሎት ወምጽዋት

ምዕራፍ ፮ ።

፩ ወባሕቱ ዑቁ ምጽዋተክሙ ኢትግበሩ ለዓይነ ሰብእ ከመ ያስተርእዩ ሎሙ ።

፩ ባሕቱን የሚጽፍም የማይጽፍም አለ ምጽዋታችሁን ሰው ይይልን ብላችሁ እንዳታደርጉ ዕወቁ ።

ወእመ አኮሰ ዓስብ አልብክሙ በኀበ አቡክሙ ዘበሰማያት ያለዚያ ግን በሰማይ አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም ።

፪ ወሶበሂ ትገብሩ ምጽዋተክሙ ኢትንፍሑ ቀርነ በቅድሜክሙ በከመ ይገብሩ መደልዋን በመራኅብት ወበአስኳት ።

፪ በምትመጸውቱበትም ጊዜ ግብዞች ሰው ሰብስበው ቀን ቀጥረው በተመሳቀለ ጎዳና ባደባባይ እንዲያደርጉት ቀን ቀጥራችሁ ዐዋጅ ነግራችሁ አታድርጉት ። አንድም ውዳሴ ከንቱ ሽታችሁ አታድርጉት ። አንድ ባለጸጋ አፈ ወርቅን እንደጠየቀው ይሆን ሲያስተምር አንድ ባለጸጋ መጥቶ ምጽዋት መመጽወት እወዳለሁ ውዳሴ ከንቱም እወዳለሁ አለው ውዳሴ ከንቱውን ትተህ መጽውት አለው አይሆንም ሁሉንም እወዳለሁ ይህ ከቀረ ምጽዋቱም ይቅር አለው እንኪያስ አትተው መጽውት ሰው ዘር ይዘራል ባይጠብቀው የእሸት ያህል ያጣለታልን አንተም የዚያን ያህል ጥቂት ዋጋ አታጣም ሰጥ ብሎታል ።

ከመ ይትአኰቱ እምኀበ ሰብእ ሰው ያይላቸው ይሰማላቸው ዘንድ ።

አማን እብለክሙ ኃጕሉ ዕሤቶሙ ።

ኃጕሉ ቢል የወዲያኛውን ዋጋቸውን አጡ ነሥኡ ይላል ውዳሴ ከንቱን አገኙ ብየ እንዳገኙ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፫ ወአንተሰ ሶበ ትገብር ምጽዋተከ ኢታእምር ፀጋምከ ዘትገብር የማንከ ።

፫ አንተ ግን በምትመጸውትበት ጊዜ ቀኝ እጅህ የምትሠራውን ግራ እጅህ አትወቀው ። ማለት በቀኝ እጅህ የያዝከውን በግራ እጅህ አትያዘው ግራ ደካማ ነው ጥቂቱን ብዙ ያስመስለዋል ልክፈልለት ያሰኛልና ቀኝ ኃያል ነው ብዙውን ጥቂት ያስመስላል ፤ ከዚህ ምን እከፍልለታለሁ ልስጠው ያሰኛልና ፡ አንድም ሚስትህ አትወቅብህ ሲለው ነው ፀጋም አላት የባልና የሚስት ከብት ሎሚ ከሁለት እያለች ታዳክ ማለችና እንዳታዳክመው ከሚስት የሚሠወር ምን አለ ቢሉ ቅንነቱማ ካለ ገንዘቡ ሁሉ ያለ በእሱ እጅ አይደለምን ከዚያው ይስጥ ይህማ ስርቆት አይሆንበትም ቢሉ ሰጥቶ ይንገራት አይሆንም ብትለውሳ ቢሉ ይለ ያዩ ጥንቱን መጋባታቸው ሰጥተው መጽውተው ሊጸድቁ ነውና ። አንድም ልጆችህ ዐይወቁብህ ሲል ነው ዐጋም አላቸው ያባታችን የቁም ወራሽ የሙት አልቃሽ እያሉ ያዳክማሉና እንዳያዳክሙት አንድም ቤተሰቦችህ ዐይወቁብህ ፀጋም አላቸው የጌታችን ወርቁ ለዝና ልብሱ ለእርዝና እህሉ ለቀጠና እያሉ ያዳክማሉና እንዳያዳክሙት ።

፬ ከመ በኅቡእ ይኩን ምጽዋትከ ፤

፬ ምጽዋትህ በስውር ይሆን ዘንድ ።
ወአቡከ ዘይሬእየከ በኅቡእ የአስየከ ክሡተ ። ስትመጸውት ተሰውሮ የሚያይህ አንድም ተሰውረህ ስትመጸውት የሚያይህ ሰማያዊ አባትህ ጉባኤውንስ ከሻኸው በጻድቃን በሰማዕታት በመላእክት በኃጥአን በአጋንንት ፊት ገልጾ ዋጋህን ይሰጥሃል ።

፭ ወሶበሂ ትጼልዩ ኢትኩኑ ከመ አሕዛብ ።

፭ በምትጸልዩበትም ጊዜ እንደ ግብዞች አትሁኑ እስመ ያፈቅሩ በመኳርብት በውስተ መዓዝነ መራ ህብት ቀዊመ ወጸልዮ ከመ ያስተርእዩ ለዓይነ ሰብእ ሰው ይይልን ሰው ይስማልን ብለው በምኩራብ ባደባባይ ቁሞ መጸለይን ይወዳሉና ፡ በምኩራብማ መጸለይ እንዲገባ ለማጠየቅ ሙሴን ወንድምህ አሮን ድምጽ ያለው ልብስ ለብሶ ያን እያሰማ ገብቶ ይጸልይ ሕዝቡም እሱን አብነት አድርገው ገብተው ይጸልዩ ብሎት የለምን ቢሉ ከዚያው መካነ ጸሎት መካነ ትምህርት መካነ ተማኅጽ አለ ፡ እኒህ ግን መካነ ጸሎቱን ትተው በመካነ ተማኅጽ ቆመው ይታያሉና ። አማን እብለክሙ ኃጕሉ ዕሤቶሙ ።

፮ እንዳለፈው በል ፤
ወአንተሰ ሶበ ትጼሊ ባእ ቤተከ ወዕጹ ሆኅተከ ወጸሊ ለአቡከ ።

፮ አንተ ግን በምትጸልይበት ጊዜ ከቤትህ ገብተህ ደጅህን ዘግተህ ወደ ሰማያዊ አባትህ ጸልይ ። አንድም በምትጸልይበት ጊዜ ሕዋሳትህን ሰብስበህ በሰቂለ ሕሊና በነቂሐ ልቡና ሁነህ ወደ ሰማያዊ አባትህ ወደ እግዚአብሔር አመልክት ።

ወአቡከ ዘይሬእየከ በኅቡእ የዓሥየከ ክሡተ ። ተሰውረህ ስትጸልይ የሚያይህ ሰማያዊ አባትህ ዋጋህን ይሰጥሃል ወእንዘ ትጼልዩ ።

፯ ኢትዘንግዑ ከመ አሕዛብ ።

፯ ስትጸልዩ እንደ አሕዛብ አብዝታችሁ አትጸልዩ ። ግብር ዘአልቦ ምግባኔ ነገር ውእቱ ወለነገርኒ ይተልዎ ዝንጋኤ እንዲል አንድም ጨሃችሁ አትጸልዩ ኢትከላህ በሕቁ አላ ዘምር በመጠን ከመ ኢይዘንግዑ አኃው እንዲል ።
እስመ ይመስሎሙ በአብዝኆ ንባቦሙ ዘይሰምዖሙ አብዝተው ጮኸው በመጸለያቸው የሚሰማቸው ይመስላቸዋልና ።

፰ ኢትትመሰልዎሙኬ ፤

፰ አብነት አታድርጓቸው ፡ እስመ የአምር አቡክሙ ሰማያዊ መፍቅደክሙ ዘእንበለ ትስአልዎ ፤ እናንተስ አብዝታችሁ ጨሃችሁ ሳትለምኑት ሰማያዊ አባታችሁ የምትሹትን ዐውቆ ያደርግላችኋል ።

፱ አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ ከመዝ በሉ ።

፱ ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፪ እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ እንዲህ በሉ ። ሐተታ አብዝታችሁ አትጸልዩ ብሎ ነበርና አጭር ጸሎት ጨኽችሁ አትጸልዩ ብሎ ነበርና የሕሊና ጸሎት ቋሚ ለኅሚ ገረድ ደንገጽር ሲቆሙ ሲቀመጡ ሲተኙ ሲነሡ የሚጸልዩት አጭር ጸሎት ሠራልን ።
አቡነ ዘበሰማያት ።
በሰማይ ያለህ አባታችን ፡ አቡነ በሉኝ አለ አምላክነ እግዚእነ መምህርነ በሉኝ አላለም ቀድሞ ነቢያት ከግብርናተ ዲያብሎስ እንዳልወጡ ሲያጠይቅ አምላክነ እያሉ ይጸልዩ ነበር እኛ ግን ከግብርናተ ዲያብሎስ እንዳወጣን ሲያጠይቅ አቡነ በሉኝ አለ እግዚእነ መምህርነ በሉኝ አላለም ። ጌታ ሎሌውን መምህር ደቀ መዝሙሩን ቢወደው ያበላዋል ያጠጣዋል የልቡናውንም ምሥጢር ያጫውተዋል እንጂ ርስቱን አያወርሰውም ርስቱን ግን የሚያወርስ ለልጁ ነው ። እሱ ግን የማታልፍ ርስቱን መንግሥተ ሰማያትን ያወርሰናልና ። አንድም ወበከመ ይምህር አብ ውሉዶ ከማሁ ይምህሮሙ እግዚአብሔር ለኵሉ ይፈርህዎ እንዲል አባት ለልጁ እንዲራራ ይራራልናልና ፡ ዘበሰማያት አለ ከምድራዊ አባት ሲለይ ምድራዊ አባት ሲወልድ በግዘፍ ሲያሳድግ በግዘፍ ነው ኋላም ኃላፊ ርስቱን ያወርሰዋል ኋላ ሞትን ያስከትልበታል እሱ ግን ሲወልደን በረቂቅ ሲያሳድገንም በረቂቅ ነው ኋላም የማታልፍ ርስቱን መንግሥተ ሰማይን ያወርሰናል ኋላም ሐይው ከመ መላእክትን ያስከትልልናልና ፡ አንድም ጌታ በሁሉ ምሉእ ሲሆን ስለልዕልናው በሰማይ አለ ይባላልና ዘበእንተ ዕበይከ ቸችሚሰል በደመናት እንዲል፡

እንድም ጸሎቱ በስቂለ ሕሊና ይሁን ሲል እንዲህ አለ ፤
ይትቀደስ ስምከ ፥
ስመ ወላዲ ስመ ተወላዲ ስመ ሠራጺ ይለይልን በሉኝ ። እንድም ስምየሰ መሐሪ ወመስተሣህል ያልኸው ይጽናልን በሉኝ ። እንድም መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው ስምህን አመስግነው ቅድስናህን ተሳትፈው እንዲኖሩ እኛም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለን አመስግነንህ ቅድስናህን ተሳትፈን እንድንኖር አድርገን በሉኝ አለ ።

፲ ትምጻእ መንግሥትከ ፤

፲ መንግሥተ ሰማይ ትምጣልን በሉኝ ትምጻእ ማለቱ ግን ከወዲያ ያለች ከወዲህ የሌለች ሁና ከወዲያ ወዲህ የምትመጣ ፥ ከወዲህ ያለች፥ ከወዲያ የሌለች ሁና ከወዲህ ወዲያ የምትሄድ ሁና አይደለም ትገልጽልን በሉኝ ሲል ነው እንጂ አኮ እምካልዕ መካን ዘይመጽእ ለአስተርእዮ ኀቤሆሙ አላ ሀሎ ኀቡአ ወምሉአ ማእከሌሆሙ ወውሣጤሆሙ እንዲል እንድም ልጅነት ትሰጠን በሉኝ ሲል ነው ። መተርጕምኒ ሰመያ ለትምጻእ መንግሥትከ ሱታፌ መንፈስ እንዲል ፥ ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ። መላእክት በሰማይ ሊያመሰግኑህ ፈቃድህ እንደሆነ እኛም እናመሰግንህ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን በሉኝ እንድም ኋላ ሙተን ተነሥተን ልናመሰግንህ ፈቃድህ እንደሆነ ዛሬም በሕይወተ ሥጋ ሳለን እናመስግንህ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን በሉኝ ከማሁ ማንሻ እንድም መላእክት በሰማይ አመስግነውህ ያው ምስጋናው ምግብ ሆኑዋቸው እንዲኖር ።

፲፩ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለዕለትነ ሀበነዮም

፲፩ ዘፍጥ ፳፰ ፥ ፳ ምሳ·፴·፰·፰ ጢሞ·፮ ፥ ፰ ማር ይስ· ፲፪ ፃም ለኛም በዚህ ዓለም ሳለን የዕለት ምግባችንን ስጠን በሉኝ በዚህም መጻሕፍት ተባብረውብታል ያዕቆብ በኦሪት እምከመ ረከብኩ እክለ ዘእበልዕ ወልብሰ ዘእትኤረዝ ይኩነኒ እግዚአብሔር አምላኪየ ብሏል ጳውሎስም እምከመ ረከብነ ሲሳየነ ወአራዘነ የአክለነ ብሏል ። ፫ቱ ምእትም በሕንጸ መነኮሳት ኢትኩን መፍቀሬ ወርቅ ወብሩር ዘእንበለ በአምጣነ ዘየአክል ለሕይወትከ ለሲሳይከ ወለአራዝከ በዐቅም ብለዋል ። ማር ይስሐቅም እመቦ ዘተርፈ እምፍቃደ ዕለትከ ሀቦ ለነዳይ ብሏል ፥ ለፍጹማን የሆን እንደሆነ በቁሙ የዕለት ምግብ ነው ። ለሰብአ ዓለም ግን ያመት ልብስ ያመት ምግብ ዘር አስቀርቶ የቀረውን መስጠት ነው ። እንድም ሥጋህን ደምህን ንስሐን ትምህርትን ዓስበ ጸሎታችንን ስጠን በሉኝ ።

፲፪ ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኀድግ ለዘአበሰ ለነ ።

፲፪ እኛም የበደለንን ይቅር አንል ዘንድ በደላችንን ይቅር በለን በሉኝ ፥ ይህማ ማስተሳለፍ አይሆንም ቢሉ አይሆንም ሰው ይቅር ማለቱ እኔንም እግዚአብሔር ይቅር ይለኛል ብሎ ነውና ፥ እንድም ከአኃው አንዱ ተነሥቶ አብሑኒ ከመ እወስከ አሐደ ቃለ ላዕለ አቡነ ዘበሰማያት አላቸው ። አባሕናከ ንብብ አሉት ረስየነ ያለበት ነው ብሏል ። ይቅር ማለቱ ቅሉ ያጓት ፈቃድ አይሆንም ሲል ፤

፲፫ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ።

፲፫ አቤቱ ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት ወደ መከራ ወደ ገሃነም አታግባን በሉኝ ።
አላ አድኅነነ ወባልሃነ እምኵሉ እኩይ ።
ከኃጢአት ከክህደት ከመከራ ከገሃነም አድነን እንጂ።
እስመ ዘአከ ይእቲ መንግሥት መንግሥተ ሰማይ ገንዘብህ ናትና ፤
ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም ክሃሊነት ጌትነት ለዘላለሙ ገንዘብህ ናትና ፥ አሜን በውነት ።

፲፬ እስመ ለእመ ኃደግሙ ለሰብእ አበሳሆሙ የኃድግ ለክሙኒ አበሳክሙ አቡክሙ ሰማያዊ ፤
ሲራክ ፳፰ ፥ ፫፬ ፥ ፩ ማቴ ፥ ፲፰ ፥ ፴፭ ማር ፥ ፲፩ ፥ ፳፭

፲፬ እናንተ ይቅር ብትሉ ሰማያዊ አባታችሁ የናንተንም ኃጢአት ይቅር ይላችኋልና ይቅር ይላችሁ ዘንድ ይቅር በሉ ።

፲፭ ወእመሰ ኢኃደግሙ ለሰብእ አበሳሆሙ ለክሙኒ ኢየኃድግ አበሳክሙ አቡክሙ ሰማያዊ

፲፭ የሰውን ኃጢአት ይቅር ባትሉ ግን ሰማያዊ አባታችሁ ይቅር አይላችሁምና ይቅር ይላችሁ ዘንድ ይቅር በሉ እንድም ይቅር ብጥሉ ይቅር ይላችኋል ይቅር ባትሉ ይቅር አይላችሁም አብዝታችሁ አትጸልዩ ብሎ ነበረና አጭር ጸሎት ጨኸችሁ አትጸልዩ ብሎ ነበርና የሕሊና ጸሎት ቋሚ ሰኋሚ ገረድ ደንገጽር ሲቆሙ ሲቀመጡ ሲተኙ ሲነሡ በ፯ቱ ጊዜያት የሚጸልዩት አጭር ጸሎት ሠራልን ። እንዲህ ግን ስሰሆነ ከ፹፩ መጻሕፍት ያለ ፭ ነገር አለበት ሃይማኖት ተስፋ ፍቅር ትሕትና ጸሎት ሃይማኖት ያላዩትን እግዚአብሔርን አቡነ ማለት ተስፋ ትምጻእ መንግሥትከ ማለት ፍቅር ለነ ብሎ አንዱ ላንዱ መጸለይ ትሕትና ቅዱሳን ከበቁ በኋላ ኅድግ ለነ አበሳነ ማለት ጸሎት መላው ጸሎት ነው ።

፲፮ ወሶበ ትጸውሙ ኢትኩኑ ከመ መደልዋን ።

፲፮ በምትጸልዩበት ጊዜ እንደ ግብዞች አትሁኑ እስመ እሙንቱ ይትመጻለው ወይቄጽሩ ገጾሙ ፥ ወያማስኑ ። እነዚያ ፊታቸውን አጠውልገው ግንባራቸውን ቋጥረው ሰውነታቸውን ለውጠው ይታያሉና ከመ ያእምር ሰብእ ከመ ጾሙ ።

እንደ ጾሙ ሰው ያውቅላቸው ዘንድ ።
እማነ እብለክሙ ነሥኡ ዕሤቶሙ ነሥኡ ቢል የወዲህኛውን ውዳሴ ከንቱአገኙ ኃጕሉ ቢል የወዲያኛውን ዋጋቸውን አጡት ብየ በውነት እነግራችኋለሁ

፲፯ ወአንትሙሰ ሶበ ትጸውሙ ቅብኡ ርእሰክሙ ።

፲፯ እናንተስ በምትጾሙበት ጊዜ ራሳችሁን ተቀቡ ።
ወሕፅቡ ገጸክሙ ።
ፊታችሁን ታጠቡ የተቀባ የታጠበ እንዳይታወቅበት አይታወቅባችሁ ቢል ነው ። ይህስ በጌታ ጾም ነው በጾመ ፊታድ ቢሉ በጾመ ፊቃድ ነው እንጂ በጌታ ጾምማ ምን ውዳሴ ከንቱ አለበት ፣ ይኸውስ በከተማ ነው በገዳም ቢሉ በከተማ ነው እንጂ በገዳምማ ምን ውዳሴ ከንቱ አለ ይህም ሲታወቅ ዳንኤል እምእመቦበእኩ ገዳመ ሱሳ ኢዓርገ ቅብዕ ዲበ ርእስየ ወኢቦእ ሥጋ ወወይን ውስተ አፉየ ብሏል ። እንድም ቅብኡ ፍቅርን ያዙ ቅብዕ ኢይርኅቀ ቅብዕሰ ፍቅረ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው እንዲል ፣ ወሕፅቡ ንጽሕናን ገንዘብ አድርጉ እንድም ቅብኡ ትሕትናን ያዙ ፣ ወሕፅቡ ገጸክሙ ፣ በእንብዓ ንስሐ ታጠቡ ።

፲፰ ከመ ኢያእምር ሰብእ ከመ ጾምክሙ ።

፲፰ እንደ ጾማችሁ ሰው እንዳያውቅባችሁ ።
ዘእንበለ እቡክሙ ማእምረ ኅቡእት ።
ሁሉን መርምሮ ከሚያውቅ ከሰማያዊ እባታችሁ በቀር ሰማያዊ እባታችሁ ነው እንጂ ።
ወአቡክሙ ዘይሬእየክሙ በኅቡእ የዓስየክሙ ክሡተ ። ጉባኤውን ከሻችሁ ተሰውራችሁ ስትጾሙ ተሰውሮ የሚያያችሁ ሰማያዊ እባታችሁ በጻድቃን በመላእክት በኃጥአን በእጋንንት መካከል ዋጋችሁ ይሰጣችኋል ።

፲፱ ኢትዝግቡ ለክሙ መዝገበ ዘበምድር ኀበ ይብሊ ወይማስን ፣ እንቀጸ ምጽዋት ነው ። በመካከል ፣ እንቀጸ ጾምን እንቀጸ ጸሎትን አግብቶበት ነበረና አሁን አመጣው ሰለ ሦስት ነገር ያመጣዋል ።

፲፱ እህሉን ነዳያን ሲበሉት ብለው እኑረውት ነቀዝ ቢበላው ፣ ልብሱን ነዳያን ቢለብሱት ብለው እኑረውት ነቀዝ ቢበላው ፣ ልብሱን ነዳያን ሲለብሱት ብለው እኑረውት ብል ቢበላው ምቀኝነት ነውና ፣ ዳግመኛ ለከፉ ጊዜ ይሆነኛል ብሎ ማኖር እግዚአብሔርን ከዳተኛ ማድረግ ነው ። በዝናብ አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ አይመግበኝም ማለት ነውና ፣ እንድም ምንም እጅ እግር ባያወጡስት ገንዘብ ማኖር ጣዖት ማኖር ነውና ፣ ኀልፈት ጥፋት ያለበትን ምድራዊ ድልብ አታድልቡ ።
ኀበ ጸጼ ወቁንቁኔ ያማስና ፣ ብል የሚበላውን ነቀዝ የሚያበላሸውን ።
ወኀበ ሰረቅት ይከርዩ ወይሰርቅዎ ።
ሌቦች ናሱን እፍርሰው ግድግዳውን ምሰው የሚወስዱትን ከሚወስዱት ቦታ አታድልቡ ።

፳ ዝግቡ ለክሙ መዝገበ ዘበሰማያት ኀበ ኢይበሊ ወኢይማስን ። ሉቃ ፣ ፲፪ ፣ ፴፫ ፣ ፩ ጢሞ ፮ ፣ ፲፱ ።

፳ አላ ያለበት ነው ። ኀልፈት ጥፋት የሌለበትን ሰማያዊ ድልብን አድልቡ እንጂ ።
ወህበ ኢያማስና ጸጼ ወቁንቁኔ ።
ብል የማይበላውን ነቀዝ የማያበላሸውን ።
ወኀበ ሰረቅት ኢይከርዩ ወኢይሰርቅዎ ።
ሌቦች ናሱን እፍርሰው ግድግዳውን ምሰው የማይወሰዱትን ከማይወሰዱበት አድልቡ እንጂ ።

፳፩ እስመ ኀበ ሀሎ መዝገብክሙ ሀየ ይሄሉ ልብክሙኒ ።

፳፩ ገንዘባችሁ ካለበት ዘንድ ልቡናችሁ ከዚያ ይኖራልና ፣ እንድም ፣ ኢትዝግቡ ብሄህ መልስ ውዳሴ ከንቱ ያለበትን ምጽዋት አትመጽውቱ ዘይበሊ ውዳሴ ከንቱ የሚያስቀርባችሁን ወኅበ ሰረቅት እጋንንት በውዳሴ ከንቱ የሚያስቀሩባችሁን እላ ያለበት ነው ። ውዳሴ ከንቱ የማያስቀርባችሁን ውዳሴ ከንቱ የሌለበትን ምጽዋት መጽውቱ እንጂ እጋንንት በውዳሴ ከንቱ የማያስቀሩባችሁን ምጽዋታችሁ ካለበት ልቡናችሁ ከዚያ ይኖራልና ። እስመ ዘይገብሩ ለሠናይት ይሴፈዋ ለሠናይት እንዲል ።

፳፪ ማኅቶቱ ለሥጋከ ዓይንከ ውእቱ ። ሉቃ ፣ ፲፩ ፣ ፴፬ ።

፳፪ የሥጋህ ፋና ዓይንህ ነው ማለት የሥራ መከናወኛ ዓይንህ ነው ፣
ወእምከመ ዓይንከ ብሩህ ውእቱ ኵሉ ሥጋከ ብሩሃ ይከውን ፣ ዓይንህ ብሩህ የሆነ እንደሆነ አካልህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል ዓይንህ የቀና እንደሆነ ሥራህ ሁሉ የቀና ይሆናል ።

፳፫ ወእመሰ ዓይንከ ሐማሚ ውእቱ ኵሰንታከ ጽልመተ ይከውን

፳፫ ዓይንህ የሚታመም የሆነ እንደሆነ አካልህ ሁሉ ጨለማ ይሆናል ማለት ዓይንህ ግን ያልቀና እንደሆነ ሥራህ ሁሉ ያልቀና ይሆናል ።
ወሶበ ብርሃን ዘላዕሌከ ጽልመት ውእቱ ጽልመትከ እፎ ይከውንከ ።
ባንተ ያለ ብርሃን ጨለማ ከሆነ ጨለማህ እንደምን ይሆን ፣ በተፈጥሮ የተሰጠህ ዓይንህ የታመመ ከሆነ ጨለማ እንደምን ይጸናብህ ይሆን ፣ እንድም ጽልመትከ እፎ ብርሃን ይከውነከ ፣ የታመመው ዓይንህ እንደምን ያይልሃል ፣ እንድም ማኅቶቱ ብሰህ መልስ

የሥራህ መከናወኛ አእምሮ ጠባይህ ነው ወእም ከመ ዓይንከ ፡ አእምሮ ጠባይዕህ የቀና እንደሆነ ሥራህ ሁሉ የቀና ይሆናል ወሶበ ብርሃን ፣ አእምሮ ጠባይዕህ ያልቀና እንደሆነ ሥራህ ሁሉ ያልቀና ይሆናል በተፈጥሮ የተሰጠህ አእምሮ ጠባይዕህ ያልቀና ከሆነ ፍዳ እንደምን ይጸናብህ ይሆን አንድም ጽልመትከ ያልቀና አእምሮ ጠባይዕህ እፎ ብርሃን ይከውነከ ። እንደምን መከበሪያ መጽደቂያ ይሆንሃል ። አንድም የሥራህ መከናወኛ ምጽዋትህ ነው ፣ ምጽዋትህ ውዳሴ ከንቱ የሌለበት እንደሆነ ሥራህ ሁሉ የቀና ይሆናል ። ምጽዋትህ ግን ውዳሴ ከንቱ ያለበት እንደሆነ ሥራህ ሁሉ ያልቀና ይሆናል ወሶበ ብርሃን ካንተ የሚሰጥ ምጽዋትህ ውዳሴ ከንቱ ያለበት ከሆነ ፍዳ እንደምን ይጸናብህ ይሆን ፤ አንድም ጽልመትከ ውዳሴ ከንቱ ያለበት ምጽዋትህ እፎ ብርሃን ይከውነከ እንደምን መከበሪያ መጽደቂያ ይሆንሃል ፣ አንድም የሥራህ መከናወኛ ኤጲስ ቆጶስህ ነው ። ኤጲስ ቆጶስ የቀና እንደሆነ ሥራህ ሁሉ የቀና ይሆናል ። ኤጲስ ቆጶስህ ግን ያልቀና እንደሆነ ሥራህ ሁሉያልቀና ይሆናል ፤ ኤጲስቆጶስህ ግን ያልቀና እንደሆነ ሥራህ ሁሉ ያልቀና ይሆናል ። ወሶበ ብርሃን ባንተ የተሾመ ኤጲስ ቆጶስህ ያልቀና ከሆነ ፍዳ እንደምን ይጸናብህ ይሆን አንድም ጽልመትከ ፤ ባንተ የተሾመ ኤጲስቆጶስህ እፎ ብርሃን ይከውነከ እንደምን መከበሪያ መጽደቂያ ይሆንሃል ።

፳፬ ኢይክል ፩ዱ ገብር ተቀንዮ ለ፪ኤ አጋዕዝት ከፍለን መጽውተን ከፍለን ብንኖር ምንዋ ትሉኝ እንደሆነ ። ሉቃ ፣ ፲፮ ፣ ፲፫ ።

፳፬ አንድ ባሪያ ለሁለት ጌታ መገዛት አይቻለውም ።
ወእመአኮሰ ፩ደ ይጸልእ ወካልአ ያፈቅር ፤
ይህም ባይሆን ማለት እገዛለሁም ቢል አንዱን ይጠላል አንዱን ይወዳል ፤ ወእመ አኮ ለአሐዱ ይትኤዘዝ ።

ያፈቅር ያለውን ይትኤዘዝ ይይጸልዕ ያለውን ኢይትኤዘዝ አለ ላንዱ ይታዘዛል ለአንዱ አይታዘዝም እንጂ ፣ ሐተታ ፤ አንዱ ቆላ ውረድ ሲለው አንዱ ደጋ ውጣ ቢለው ከሁለት ይሆናልን አይሆንም ሲል ። ኢትክሉኬ ተቀንዮ ለእግዚአብሔር ወለንዋይ ፡- እንደዚህም ሁሉ እናንተም ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አይቻላችሁም ። ወለንዋይ ባለው ወለማሞ ይላል ጥሬ ።

፳፭ ወበእንተዝ እብለከሙ ኢትተከዙ ለነፍስከሙ ዘትበልዑ ወዘትሰትዩ ወኢለሥጋከሙ ዘትለብሱ ። መዝ ፶፬ ፣ ፳፪ ሉቃ ፲፪ ፣ ፳፪ ፊልጵ ፬ ፣ ፮ ። ፩ ጢሞ ፮፣ ፯ ፩ ጴጥ ፭፣ ፯ ።

፳፭ ስለዚህ ነገር ለነፍሳችን ምን እንበላለን ምን እንጠጣለን ለሥጋችን ምን እንለብሳለን ብላችሁ አታስቡ መብል መጠጥን ለነፍስ ሰጥቶ ተናገረ የበሉት የጠጡት ደም ይሆናል በዚህ ምክንያት ነፍስ ከሥጋ ጋራ ተዋሕዳ ትኖራለችና ፣ እስመ ነፍስ ተጋድር በደም እንዲል ልብስን ለሥጋ ሰጥቶ ተናገረ ምንም የምታፍር ነፍስ ብትሆን አጊጾ ክብር የሚታይ ሥጋ ነውና ።

አኮሁ ነፍስ ተዓቢ እምሲሲት ምግብ ከመስጠትማ ነፍስን አምኃበ አልቦ አምጥቶ መፍጠር ጭንቅ አይሆንምን ።
ወሥጋ የዓቢ እምልብስ ።

ልብስ ከመስጠትማ ሥጋን ካራቱ ባሕርያት አዋሕዶ መፍጠር ጭንቅ አይሆንምን ፣ ነፍስን እምኀበ አልቦ አምጥቼ ሥጋን ካራቱ ባሕርያት አዋሕጄ የፈጠርኋችሁ ለናንተ ምግብ ልብስ እንደምን እነሣችኋለሁ ለማለት እንዲህ አለ ። አንድም አኮሁ ብለህ መልስ ፣ ለናንተ ምግብ ከመስጠትማ ነፍስን ካለችበት ማምጣት ጭንቅ አይሆንምን ? ወሥጋ የዓቢ ፣ ልብስ ከመስጠትማ ሥጋን ካለበት ማንሣት ጭንቅ አይሆንምን ? ነፍስን ካለችበት አምጥቼ ሥጋን ካለችበት ኋላ በመንግሥተ ሰማይ መንፈሳዊ ምግብ የምመግባችሁ ዛሬ ለናንተ ምግብ ልብስ እነሣችኋለሁን ለማለት ፣ አንድም ወበእንተዝ እብለከሙ ብለህ መልስ ሥጋውን ደሙን ወለሥጋከሙ ዘትለብሱ ። ልጅነትን ማን ይሰጠናል ብላችሁ አታስቡ ሥጋየን ደሜን ከመስጠትማ ነፍስን ሥጋን መዋሐድ ጭንቅ አይሆንምን ነፍስን ሥጋን የተዋሐድሁላችሁ ፡ ሥጋየን ደሜን እነሣችኋለሁን ለማለት እንዲህ አለ ፡ ጭንቅነቱ በሌላ ነው እንጂ በሱ አይደለም

፳፮ ነጽሩ አዕዋፈ ሰማይ እለ ኢይዘርዑ ወእለ ኢየዓርሩ ወኢያስተጋብኡ ውስተ አብያት ወአቡከሙ ሰማያዊ ይሴስዮሙ ።

፳፮ ከፍለን መጽውተን ከፍለን ካላኖርን ምን እንመገባለን ትሉኝ እንደሆነ ዘር መከር የሌላቸውን በጎታ በጎተራ በረቅ የማይሰበስቡን ሰማያዊ አባታችሁ የሚመግባቸው አዕዋፍን እዩ ማለት አዕዋፍን አብነት አድርጉ ። ከመ ኢይዘርዑ ይላል ዘር መከር እንደሌላቸው በጎታ በጎተራ በረቅ እንዳይሰበስቡ ሰማያዊ አባታችሁ እንዲመግባቸው ዕወቁ ።
አኮኑ አንትሙ ፈድፋደ ትኄይስዎሙ ።

ለኒያማ እንዴታ ትሉኝ እንደሆነ ከተፈጥሮተ አዕዋፍማ ተፈጥሮተ ሰብእ አይበልጥምን ለኒያ ምግብ የሰጠ ለናንተ ይነሣችኋል ለማለት እንዲህ አለ ታሪክ እንደ ሁለት መነኰሳት ይኸን ይዘው በተባሕትዎ ሁነው በረኃብ በጽምዕ የሚያልቁ ሁነዋል ። ኋላ መልአክ አለ ኢይዘርዑ አለ እንጂ አለ ኢይሰርሩ አለ አላቸው ከዚህ በኋላ ተግባረ እድ ይዘው ራሳቸውን ረድተው የሚኖሩ ሁነዋል ። ከአባ ስልዋኖስ ገዳም እንደ ገባ መነኰሴ እንደምን ሁናችሁ ትኖራላችሁ

አላቸው ተግባረ አድ ይዘን እንኖራለን አሉት ። እናንተስ ወንጌላውያንም አይደላችሁ ጌታ በወንጌል ነጽሩ አዕዋፈ ሰማይ ቢል አላቸው ፥ ይህ ነገሩ ሲላሳብ ከአበ ምኔቱ ደረሰ እናንተ ሥራችሁን አትተው ስሱም የሚሻውን መጽሐፍ በጡት ይመልከት አላቸው ። ቦታ መጣፍ ሰጥተውት ሲመለከት ዋለ ፥ ምግብ የሚመገቡ በደወል ነውና ፤ ደወል አትምቱ ጊዜያት አይታችሁ ተመገቡ አላቸው ። ጊዜያት አይተው ተመገበው በየበዓታቸው ሔዱ ። ይጠሩኛል ብሎ ቢያይ የማይጠሩት ሆነ ተደሩት እኃው እያለ እሱ ካለበት ሄደ ፤ እወ ተደሩ ኢለው በሀገራችሁ አንግዳ አኑሮ መብላት ሥራትን ነው አለው ፤ አንተግ መንፈሳዊ ነህ አትሻውም ብለን እኛ ሥጋውያኑ ተመገብነው አለው ፤ አባቴ አላበጀሁም ብሎ አነሱን መስሎ የሚኖር ሁነዋል ። አንድም ነጽሩ ብለህ መልስ ዘር መከር የሌላቸውን ሰማያዊ አባታችሁ የሚመግባቸው እሥራኤልን አብነት አድርጉ እንዲመግባቸው ዕወቁ እሥራኤል ልብስ አላለቀ በትርሀ አልወደቀ እንዲሉ ፤ ከውቂያኖስ በደመና አይበት ተቋጥሮ በነፋስ ወደልጋዝ ተጭኖ መጠኑ ድምብላል አህሎ መልኩ በረድ መስሎ ወእንዘ የኃድግ ህቦ ይላል የውርጭ ገበታ ሲነጠፍ እየዘነ መላቸው ፵ ዘመን መናውን ተመግበዋል ።
አኮኑ አንትሙ ትኄይስዎሙ ።
ለኒያማ እንዴታ ትሉኝ እንደሆኑ በዘመነ ብሉይ ከነፀሩ ከኒያማ በዘመነ ሐዲስ ያላችሁ እናንተ ትበልጡ የለምን ለኒያ የሰጠው ለናንተ እንሚችኋለሁ ለማለት እንዲህ አለ ። አንድም ነጽሩ ብለህ መልስ ትንቢት ያልተነገረላቸውን ሱባዔ ያልተቈጠረላቸውን ሰማያዊ አባታችሁ ሥጋውን ደሙን የሚመግባቸው አሕዛብን አብነት አድርጉ እንዲመግባቸው ዕወቁ ። ለኒያማ እንዴታ ትሉኝ እንደሆነ ትንቢት ካልተነገረላቸው ሱባዔ ካልተቈጠረላቸው ከአሕዛብማ ትንቢት የተነገረላችሁ ሱባዔ የተቈጠረላችሁ እናንተ የምትበልጡ አይደለምን ።

፳፯ መኑ እምኔክሙ በተከዞ ዘይክል ወስኮ በዲበ ቆሙ አሐደ እመተ ።

፳፯ በዚያውስ ላይ ራሳችሁንማ አስባችሁ ታሳድሩ ዘንድ ከናንተ ወገን እጠርሁና ልርዘም ብሎ በቁመቱ ላይ ከንድ ሙሉ ቁመት መጨመር የሚቻለው ማነው እንደዚህም ሁሉ በቃሁ ነቃሁ ብሎ ሥልጣነ ክህነትን ለራሱ ገንዘብ ማድረግ የሚቻለው ማነው ።

፳፰ ወበእንተ ዓራዝኒ ምንተኑ ትሔልዩ ።

፳፰ የልብሱንስ ነገር ለምን ታስባላችሁ ። ርእዩ ጽጌያተ ገዳም ዘከመ ይልሕቁ ኢይጻምው ወኢይፈትሉ ።
ሳይደክሙ ሳይፈትሉ እንዲያድጉ ማለት ገዳማት ዕፀዋትን ዕፀዋት ጽጌያትን ጽጌያት መወደድን አጊጸው እንዲኖሩ ዕወቁ ።

፳፱ እብለክሙ ከመ ሰሎሞን ጥቀ ኢለብሰ በኵሉ ክብሩ ከመ ፩ እምእሉ ።

፳፱ ሰሎሞንስ እንኳ በዚያ ሁሉ ባለጠግነቱ ከጽጌያት እንዳንዱ አለበሰም ብየ እንዳለበሰ እነግራችኋለሁ ። ሐተታ አበባ ያለበት ቀሬማ የተሳበበት ወርቀ ዘቦ ግምጃ ይለብስ አልነበረም ቢሉ የሱ የባሕርዩ አይደለም የእሳቸው ግን የባሕርያቸው ነውና እሱ እነዚያን አብነት አድርጎ ነው ፤ እነዚያ ግን እሱን አብነት አያደርጉምና በኵሉ ክብሩ ማለቱ ብፅልን ካንተ ፀፊት እንዳልተነሣ ካንተም በኋላ እንዳይነሣ አድርጌ ሰጥቸሃለሁ ብሎታልና ፤ አንድም ወበእንተ አራዝኒ ብለህ መልስ የልጅነትን ነገር ለምን ታስባላችሁ ትንቢት ያልተነገረላቸው ሱባዔ ያልተቈጠረላቸው ልጅነትን ያገኙ አሕዛብን አብነት አድርጉ ። እብለክሙ ከመ ሰሎሞን እሥራኤልን በመከበባቸው ሰሎሞን አላቸው እሥራኤልስ እንኳ በዚያ ሁሉ ትንቢት በዚያ ሁሉ ሱባዔ ከአሕዛብ እንዳንዱ ልጅነትን አላገኙም ብየ እንዳላገኙ እነግራችኋለሁ ።

፴ ወናሁ ሣዕረ ገዳም ዘዮም ሀሎ ወጌሠመ ውስተ ዕቶነ እሳት ይትወደይ ወእግዚአብሔር ዘከመዝ ያለብሶ ።

፴ የሚያስተምርበት ደጋ ነው ቢሉ ነገ በቆላ መንደድ ጸዐቶ ከረምት ነው ቢሉ ነገ በበጋ መንደድ የሚነድ ሣዕረ ገዳምን ዛሬ በልምላሜ የሚያኖር እግዚአብሔር ፤

እፎ እንከ ፈድፋደ ኪያክሙ እሕጹፃነ ሃይማኖት ፤ እናንት ሃይማኖት የሌላችሁ ለናንተማ እንደምን ልብስ ምግብ ይነሣችኋል ፤ ወሊአመ ኮነ ሥርወ ጽጌ ይላል ፥ በሉቃስ ሥርወ ጽጌ ዛሬ በልምላሜ የሚኖር ከሆነ ኋላ በቆላ መንደድ የሚነድ ከሆነ እግዚአብሔርም እንዲህ በልምላሜ የሚያኖረው ከሆነ ። እፎ ኪያክሙ አንድም ወናሁ ሣዕረ ገዳም ብለህ መልስ ዛሬ በተድላ የሚኖር ኋላ በገሃነም ፍዳ የሚቀበል አይሁዳዊን በተድላ የሚያኖር እግዚአብሔር እፎ ኪያክሙ ። አንድም አይሁዳዊ ዛሬ በተድላ የሚኖር ከሆነ ኋላ በገሃነም ፍዳ የሚቀበል ከሆነ እግዚአብሔር ይህነን በተድላ የሚኖር ከሆነ እፎ ኪያክሙ እናንት ሃይማኖት የሌላችሁ እናንተንማ እንደምን ቸል ይላችኋል ።

፴፩ ኢትተክዙኬ እንከ እንዘ ትብሉ ምንተ ንበልዕ ወምንተ ንሰቲ ወምንተ ንትከደን ።

፴፩ ምን እንበላለን ምን እንጠጣለን ምን እንለብሳለን ብላችሁ አታስቡ ።

፴፪ እስመ ዘንተሰ ኵሎ አሕዛበ ዓለም ዘእፍአ የኀሥሥዎ ፤

፴፪ ይህንስ ሁሉ ከምግባር ከሃይማኖት በእፍአ ያሉ አሕዛብ ይሹታልና ።
ወለክሙሰ የአምር አቡክሙ ሰማያዊ ከመ ትፈቅዱ ዘንተ ኵሎ ።
ለናንተስ ሰማያዊ አባታችሁ ይህን ሁሉ እንድትሹት ያውቅላችኋል ማለት ዐውቆ ይሰጣችኋል ።

፴፫ ሕ ንትሙሰ ኅሡ መቅድመ መንግሥቶ ወጽድቆ ።

፴፫ እናንተስ አስቀድሞ ሃይማኖትን ምግባርን ሹ ፤ አንድም ፡ ልጅነትን መንግሥተ ሰማይን ሹ ።
ወዝንቱ ኵሉ ይትዌሰከክሙ ።
ይህስ ሁሉ ማለት የዚህ ዓለምስ ነገር ሁሉ በእራት ላይ ዳረጐት እንዲጨመር ይጨመርላችኋል ።

፴፬ ኢትበሉኬ ለጌሠም ።

፴፬ ለነገ አታስቡ ማለት ለነገ ይሆናል ብላችሁ አታሳድሩ ።
እስመ ጌሠምሰ ትሔሊ ለርእሳ ነገ ለራሱ ያስባል ማለት የነገውን ነገ ታስቡታላችሁና ።
የአከባ ለዕለት እኪያ ወሥራኃ የዕለት ጻሯ ጋሯ ይበቃታል ፤ የበጐ ጻር የበጐ ጋር ፡ አንድም ኢትበሉ እያልክ መልስ ፤ ለነገ ያጸናናል ብላችሁ አብዝታችሁ አትመገቡ ። የነገውን ነገ ትመገቡታላችሁና ፡ አንድም ነገ እንናዘዘዋለን ብላችሁ ኃጢአታችሁን አታሳድሩ የነገውን ነገ ትናገሩታላችሁና ። የነገውንስ ነገ ትናገሩታላችሁ ።

በእንተ ትእዛዛት ።

ምዕራፍ ፯ ።

፩ ኢትኰንኑ ከመ ኢትትኰነኑ ሉቃ፡ ፮፡ ፴፯ ፡ ሮሜ ፪ ፡ ፩ ።

፩ አንቀጸ መምህራን ነው ፤ እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ ማለት ንጹሐን ሳትሆኑ አትፍረዱ

፪ እስመ በኵነኔ ዘኰነንክሙ ትትኰነኑ አንትሙ ። ማር ፬ ፡ ፳፬ ንጹሕ ሳትሆኑ ብትፈርዱ ይፈርድባችኋልና ። ይህስ አይደለም ሰማይኒ ኢኮነ ንጹሐ በቅድሜሁ ይላል ብሎ ሳትሾሙ አትፍረዱ ተሾሞ መፍረድ እንዲገባ ሙሴ በሰለጻድ ኢያሱ በአካን ፤ ቅዱስ ጴጥሮስ በሐናንያ ቅዱስ ጳውሎስ በበርያሱስ ፈርደዋል ። እስመ በኵነኔ ዘኰነንክሙ ትትኰነኑ አንትሙ ሳትሾሙ ብትፈርዱ ይፈረድባችኋልና ። ወበመሥፈርት ዘሰፈርክሙ ይሰፍሩ ለክሙ ። በሰፈራችሁበት ይሰፍሩላችኋልና ፤ በሰፈርህበት ላዳን በመዘንህበት ሚዛን እንዲሉ ።

፫ ለምንት ትሬኢ ኃሠረ ዘውስተ ዓይኑ ቢጽከ ወሠርዌ ዘውስተ ዓይንከ ኢትኔጽር ።

፫ ባንተ ዓይን ያለ ሠረገላ ያልታየህ በወንድምህ ዓይን ያለ ጉድፍ ለምን ታያለህ ።
ኢታቤይንኑ ፤
አታስተውልም ፤

፬ ወእፎ ትብሎ ለእኁከ ኅድገኒ አውፅእ ኃሠረ እምውስተ ዓይንከ ።

፬ ወንድምህን ባንተ ዓይን ያለ ጉድፍ ተወኝ ላውጣልህ ለምን ትለዋለህ ።
ወናሁ ኢትሬኢ ሠርዌ ዘውስተ ዓይንከ ፤
ባንተ ዓይን ያለውን ሠረገላ ሳታይ ።

፭ አ መድልው ቅድመ አውፅእ ሠርዌ እምውስተ ዓይንከ ።

፭ አንተ ግብዝ አስቀድመህ ባንተ ዓይን ያለ ሠረገላን አውጣ ወእምዝ ትሬኢ ከአውፅኦ ኀሠረ ዘውስተ ዓይነ እኁከ ።
ከዚህ በኋላ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ ትለዋለህ እንድታወጣለት ትሆናለህ ፤ ምንቱ ትኔጽር ብለህ መልስ በወንድምህ ልፍረድብህ እንደምን ትለዋለህ አንተ እንዲፈረድብህ ሁነህ ሳለህ አታስተውልም ፡ ወንድምህን ተወኝ ልፍረድብህ እንደምን ትለዋለህ ባንተ እንዲፈረድብህ ሁነህ ሳለህ ፤ አንተ ግብዝ አስቀድመህ አንተ እንዳይፈረድብህ ሁን ከዚህ በኋላ ወንድምህን ልፍረድብህ ትለዋለህ ፡ እንድትፈርድበት ትሆናለህ ሐተታ የወንድሙን ኃጢአት በጉድፍ የሱን በሠረገላ መስሎ ተናገረ የወንድሙን ኃጢአት የሚያውቀው በከፊል ነው የሱን ግን መላውን ነውና ዳግመኛ ልፍረድብህ በማለቱ ይፈረድበታልና ፡ አንድም ኢትኰንኑ ፡ ከጉባኤ ሳትውሉ ምሥጢር ሳታደላድሉ እናስተምራለን አትበሉ ። እናስተምራለን ብትሉ ይፈረድባችኋልና ። ወንድምህን ላስተምርህ እንደምን ትለዋለህ አንተ ሳትማር አታስተውልም ወንድምህን ተወኝ ላስተምርህ እንደምን ትለዋለህ ። አንተ ሳትማር ፡ አንተ ግብዝ አስቀድሞ አንተ ተማር ዕወቅ ። ከዚህ በኋላ ወንድምህን ላስተምርህ ትለዋለህ እንድታስተምረው ትሆናለህ ። አንድም ለራሳችሁ ጦር ሳይጠፋላችሁ ጾር የሚጠፋበትን ግብር ለሌላው እናስተምራለን አትበሉ ። ጾር ሳይጠፋላችሁ እናስተምራለን ብትሉ ይፈረድባችኋልና ። ወንድምህን ጾር የሚጠፋበትን ግብር ላስተምርህ ለምን ትለዋለህ ላንተ ጾር ሳይጠፋልህ አታስተውልም ። አንተ ግብዝ አስቀድመህ አንተ ጾር እንዲጠፋልህ ሁን ከዚህ በኋላ ወንድምህን ጾር የሚጠፋበትን ግብር ላስተ

ምርህ ትለዋለህ እንድታስተምረው ትሆናለህ ።

፮ ኢተሀቡ ቅድሳተ ለከለባት ። ማቴ ፳፭፡ ፳፱ ማር ፲፩፡ ፳፡ ፪፡ ሉቃ ፲፩፡ ፬፡ ዮሐ ፲፬፡ ፲፫፡ ያዕቆብ ፩፡ ፮ ።

፮ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ ማለት ኢትኩንኑ ካለንስ ብላችሁ ሥጋዬን ደሜን በአይሁዳዊነት ግብር ላለ ሰው አትስጡ ።
ወኢትደዩ ባሕርየክሙ ቅድመ አኅርው ፤
ዕንቋችሁንም በእሪያ ፊት አታኑሩ ።
ከመ ኢይኪድዎ በእገሪሆሙ ፤
በእግራቸው እንዳይረግጡት ።
ወተመይጦሙ ይስጥሑክሙ
ተመልሰው ይጸጓችኋል ። ሐተታ በመሬቸው ተን ዋዕየ ፀሐይ ይጸናል ። ሌሊት ዕንቍ ከተራራ ላይ አኑረው የሚጸፍ ሲጸፍ የሚያድን ሲያድን ያድራሉ። እሪያ መልክ ጥሩ ነው ባጠገቡ፤ ሲሄድ የገዛ መልኩን አይቶ ደንግጦ ሲሔድ ሰብሮት ይሄዳል ዕንቍ የጌታ እሪያ የአይሁድ ምሳሌ አሉ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን እያለ በገዛ ኃጢአታቸው ቢዘልፋቸው ጠልተው ተመቅኝተው ሰቅለው ገድለውታልና ፤ ከመ ኢይኪድዎ እንዳይነቅፉት ወተመይጦሙ አማርኛችን ካማርኛችሁ ኃይለ ቃላችን ከኃይለ ቃላችሁ እያሉ ተመልሰው ፍትሐ ርትዑ ሥላሴን ያስፈርዱባችኋልና አንድም ኢተሀቡ እያልሁ መልስ ሃይማኖታችሁን ለመናፍቅ አትንገሩ ከመ ኢይኪድዎ እንዳይነቅፉት ወተመይጦሙ ፤ አማርኛን ካማርኛችሁ ኃይለ ቃላችን ከኃይለ ቃላችሁ አንድ ነው እያሉ ይከራከሯችኋልና አንድም መልስ በተዓቅቦ ያገኛችሁትን ምሥጢር ባልበቃ ሰው አትንገሩ ሰው ሲሆን ለዚህን ይበቃሉ እንዳይሏችሁ፤ ወተመይጦሙ ተመልሰው ፍትሐ ርትዑ ሥላሴን ያስፈርዱባችኋል ።

፯ ሰአሉ ወይትወሀበክሙ ፤
የበቃውን ያልበቃውን በምን እናውቀዋለን ትሉኝ እንደ ሆነ ፣
፯ ለምኑ ይሰጣችኋል ሐተታ እንደ ዮሐንስ ዘደማስቆ ፣ እንደ ድሜጥሮስ የበቃና ያልበቃ ለይተው ይሰጡ ነበር ።
ኅሡ ወትረክቡ ።
ሹ ታገኛላችሁ ።
ጕድጕዱ ወይትረኃወክሙ ፤
አጅ ጽፉ ይከፈትላችኋል ።

፰ እስመ ኵሉ ዘሰአለ ይነሥእ ።
፰ የለመነ ሁሉ ያገኛልና ፣ ብለው ለምነው ያገኙ ብዙ ናቸው ከዚያው ግን አዳም ፤
ወዘኒ ኃሠሠ ይረክብ ፤
የሻም ያገኛልና ኀሡ ፤ ሽተው ያገኙ ብዙ ናቸው ከዚያው ግን ከቀደሙ ሰዎች አብርሃም ከኋላ ሰዎች ሙሴ ጸሊም በፀሐይ ቢሥነ ጕጥረት ተመራምረው አምነዋል ።
ወለዘኒ ጕድጕደ ይትረኃዎ ።
እጁን ለጸፋም ይከፈትለታልና ጕድጕዱ ባለው እንደ ፊያታይ ዘየማን ።

፱ መኑ ውእቱ እምኔክሙ ዘይሰእሎ ወልዱ ወእብነ ይሁቦ ፤

፱ እኛ ለሌላው በጎ ነገር ስንለምን በኛ ክፉ ነገር ቢደረግብንሳ ትሉኝ እንደሆነ ከናንተ ወገን ልጁ ዳቦ የሚለምነው አባቱ ደንጊያ የሚሰጠው ማን አለ ፤ አንድም እብነኑ ይሁብ ልጁ ዳቦ ቢለምነው ቁርሱን ይሰበረው ብሎ ደንጊያ ይሰጠዋልን ከዚያው ቅሉ ሳይላዩን ትቶ ልብ ልቡን ይሰጠው የለምን ።

፲ ወእመኒ ዓሣ ሰአሎ ወአርዌ ምድር ይሁቦ ።

፲ ከናንተ ወገን ልጁ ዓሣ የሚለምነው አባቱ እባብ የሚሰጠው ማን አለ አርዌ ምድርን ይሁቦ መርዙ ይገድለው ብሎ እባብ ይሰጠዋልን ፤ ከዚያው ቅሉ አጥንት አጥንቱን ትቶ ሥጋ ሥጋውን ይሰጠው የለም ብሉቃስ ወእመኒ አንቆቅሐ ሰአሎ አቅረበኑ ይሁብ ይላል ። ልጁ ዕንቊላል የሚለምነው አባቱ አምቧይ የሚሰጠው ማን አለ ፣ አንድም ልጁ ዕንቊላል ቢለምነው አባቱ አንቧይ ይሰጠዋልን ከዚያም ቅሉ ቅርፍት ቅርፍትን ትቶ አስኳል አስኳሉን ይሰጠው የለምን ።

፲፩ ወሶበ አንትሙ እኩያን አንትሙ ተአምሩ ሠናየ ሀብተ ውሂበ ለውሉድክሙ እፎ እንከ ፈድፋደ አቡክሙ ዘበሰማያት ይሁቦሙ ሠናይተ ለእለ ይስእልዎ ።

፲፩ ከኛ ወገን እንዲህ የሚያደርግስ የለም ትሉኝ እንደሆነ ዘአንትሙ አንዘ አንትሙ ይላል ለባሕርያችሁ ክፋት ጥመት የሚስማማችሁ ስትሆኑ እናንተ ለልጆቻችሁ በጎ ነገርን የምታደርጉላቸው ከሆነ ቸርነት የባሕርዩ የሚሆን ሰማያዊ አባታችሁማ በጎ ነገርን ለሚለምኑት እንደምን በጎ ነገርን ያደርግላቸው ይሆን ።

፲፪ ኵሎኬ ዘትፈቅዱ ይግበሩ ለክሙ ሰብእ ከማሁ አንትሙኒ ግበሩ ሎሙ ።

፲፪ ሰዎች ሊያደርጉባችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም አድርጉላቸው እስመ ከማሁ ኦሪትኒ ወነቢያትኒ ኦሪት ነቢያት እንዲህ ብለዋልና ባኡ ማንገሽ፤

፲፫ ባኡ እንተ ጸባብ አንቀጽ ።

፲፫ ኦሪትም ነቢያትም ባኡ እንተ ጸባብ አንቀጽ ብለዋልና ወደ ጸባብ በር ግቡ በጸባብ መንገድ ሂዱ ።

እስመ ርሒብ አንቀጽ ወስፉሕት ፍኖት እንተ ትወስድ ውስተ ኃጕል ።

ወደ ጥፋት የምታደርስ ሰፊ በር ሰፊ መንገድ አለችና፤ ወብዙኃን እሙንቱ እለ ይበውኡ ውስቴታ ፤ ወደርሷ የሚገቡ ብዙ ናቸው ።

፲፬ ጥቀ ጸባብ አንቀጽ ወጽዕቅት ፍኖት እንተ ትወስድ ውስተ ሕይወት ።

፲፬ ወደ ሕይወት የምታደርስ እጅግ ጭንቅ በር እጅግ ጭንቅ መንገድ አለችና ።
ወውኁዳን እሙንቱ እለ ይበውእዋ ፤

ወደሷ የሚገቡ ጥቂት ናቸውና ሰፊውን በር ሰፊውን መንገድ ትታችሁ በጸባብ በር በጸባብ መንገድ ሂዱ ። ሐተታ ሰፊ በር ሰፊ መንገድ የተባለች ኦሪት ናት ለእመ ዓቀብከ ኦሪተከ ትበልዕ ከራሚከ ወይሰፍሕ ማኅበብተ ወያንከ ወትሬኢ ውሉደ ውሉድከ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ትላለችና ጠባብ በር ጭንቀ መንገድ የተባለች ወንጌል ናት ለዘሂ ጸፍዓከ መልታሕቴከ እንተ የማን ሚጥ ሎቱ ካልዕታሂ ወለዘሂ እስጠከ አሐደ ምዕራፈ ሑር ምስሌሁ ወአብጽሖ ሎቱ ፪ተ ምዕራፈ ወለዘሂ ይፈቅድ ይትዓገልከ መልበስከ ኅድግ ሎቱ ከዳንከሂ ትላለችና ። አንድም ሰፊ በር ሰፊ መንገድ የተባለ ፈቃደ ሥጋ ነው ጠባብ በር ጠባብ መንገድ የተባለች ፈቃደ ነፍስ ናት። አንድም ሰፊ በር ሰፊ መንገድ የተባለ ባለጸጋን መጽውት ድኃን ጹም ማለት ነው፤ ጠባብ በር ጠባብ መንገድ ባለጸጋን ጹም ድኃን መጽውት ማለት ነው ። አንድም ሰዝራ ያያት መንገድ ናት ። የሚና እሳት ወፀጋማ ቀላይ ወኢታገምር ዘእንበለ ኪደተ ፩ዱ እግረ ብእሲ እንዲል ያለንድ ጫማ የማታበቆም መንገድ አይቷል ፤ እሷ ቅሉ በሕገ ነፍስ ካልሆኑ እትገባም ሲል ነው እንጂ በቁሙ አይደለም ከዚህም ጌታችን የጸድቃን ማነስ የኃጥአን መብዛት እያሳዝነውም ጥቂት ቶንቶ ያለው ብዙ ወርቅ ባለው ጥቂት ወርቅ ያለው ብዙ ብር ባለው ጥቂት ብር ያለው ብዙ ብረት ባለው ጥቂት ብረት ያለው ብዙ ሸክላ ባለው ጥቂት ሸክላ ያለው ብዙ ደንጊያ ባለው እንዳይቀጭ ።

፲፭ ተዓቀቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት እለ ይመጽኡ ኀቤክሙ በአልባሰ አባግዕ ።

፲፭ የበግ ለምድ ለብሰው ማለት እውነተኞች መስለው ከሚመጡ ከሐሰተኞች የይማኖታውያን መስለው ከሚመጡ ከመናፍቃን መንፈሳውያን መስለው ከሚመጡ ከሥጋውያን መምህራን ተጠበቁ ። ወእንተ ውስጦሙሰ ተኩላት መሰጥ እሙንቱ ። በውስጥ ግን ነጣቂ ተኩላ ናቸው ማለት ቢመረምሯቸው ግን ሰውን እየነጠቁ ወደ ገሃነም የሚያወርዱ ናቸው ። በከመ ይቤ ኢዮብ የሚል አብነት ይገኛል ተናግሮ ሳይጸፍ የቀረ ነው ።

፲፮ ወእምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ ፤ እውነተኛ መስለው የሚመጡ ሐሰተኞችን ሃይማኖታውያን መስለው የሚመጡ መናፍቃንን መንፈሳውያን መስለው የሚመጡ ሥጋውያኑን መምህራን በምን እናውቃቸዋለን ትሉኝ እንደሆነ በሥራቸው ታውቁአሳችሁ ።

፲፮ ይቀስሙሁ እምአስዋክ አስካለ ወእምአሜከላ በለሰ ።
በዚያውስ ላይ ሥራቸውን አንሠራም እንጂ ትምርታቸውንማ ብንማርም ምን ዕዳ ይሆናል ትሉኝ እንደሆን ከሾህ ፍሬን ከደንደር በለስን ይለቅማሉ ከመናፍቅ መምህር ሃይማኖትን ከሥጋዊ መምህር መንፈሳዊ ትምህርትን ከሐሰተኛ መምህር እውነተኛ ትምህርትን ይማራሉን ፥ ከማሁ ፤

፲፯ መርዝ መርዝን ኮሶ ኮሶን እንዲያፈራ ፤ መናፍቅ መምህር ክህደትን ኑፋቄን ሥጋዊ መምህር ሥጋዊ ትምርትን ሐሰተኛ መምህር ሐሰትን እንዲያስተምር ።

፲፯ ኵሉ ዕፅ ሠናይ ፍሬ ሠናየ ይፈሪ ።
ወይን ወይንን በለስ በለስን ታፈራል ፤ ሃይማኖታዊ መምህር ሃይማኖትን መንፈሳዊ መምህር መንፈሳዊ ትምህርትን እውነተኛ መምህር እውነተኛ ትምህርትን ያስተምራል ።
ወእኩይሰ ዕፅ ፍሬ እኩየ ይፈሪ ።
መርዝ መርዝን ኮሶ ኮሶን ያፈራል ፥ መናፍቅ መምህር ክህደትን ሥጋዊ መምህር ሥጋዊ ትምህርትን ሐሰተኛ መምህር ሐሰትን ያስተምራል ።

፲፰ ኢይክል ዕፅ ሠናይ ፍሬ እኩየ ፈርየ ፤
፲፰ ወይን ኮሶን በለስ መርዝን እያፈራም ። የይማኖታዊ መምር ክህደትን መንፈሳዊ መምር ሥጋዊ ትምርትን አያስተምርም ፥ ወኢዕፅ እኩይ ፍሬ ሠናየ ፈርየ ኮሶ ወይንን መርዝ በለስን አያፈራም መናፍቅ መምህር ሃይማኖትን ሥጋዊ መምህር መንፈሳዊ ትምህርትን አያስተምርም ።

፲፱ ኵሉ ዕፅ ዘኢይፈሪ ፍሬ ሠናየ ይገዘምዎ ። ማቴ ፲፫ ።

፲፱ በጐ ፍሬ የማያፈራውን ዕንጨት ሁሉ ይቆርጡታል ።
ወውስተ እሳት ይወድይዎ ።
ከእሳትም ይጨምሩታል ። አንድም በጐ እም፣ በጐ ሥራ የማይሠራውን ሁሉ ሥላሴ ነፍሱን ከሥጋው ይለዩታል በገሃነም ፍዳ ያጸኑበታል ።
፳ ወእምፍሬሆሙሰ ተአምርዎሙ ።
፳ ቢርቀው ቢያምረው ደገመው አኮ ኵሉ ዘይብለኒ እግዚኦ ።
፳፩ እግዚኦ ዘይበውእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ። ማቴ ፳፭ ፥ ፲፩ ፥ ሉቃ ፥ ፮ ፥ ፵፮ ።

፳፩ ሁሉ አቤቱ አቤቱ ይልሃል የሚገባውንስ የማይገባውንስ በምን እናውቀዋለን ትሉኝ እንደሆነ አቤቱ አቤቱ የሚሉኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት አይ ገባም ። አኮ ዘይበውእ ። የሚገባ አይደለም ። ዘእንበለ ዘይገብር ፈቃዶ ለአቡየ ዘበሰማያት ፤ የሰማያዊ አባቴን ፈቃድ የሠራ ይገባል እንጂ ።

፳፪ ወብዙኃን ይብሉኒ በይእቲ ዕለት እግዚኦ እግዚኦ ።

፳፪ በዕለተ ምጽአት ብዙ ሰዎች አቤቱ አቤቱ ይሉኛል ።

አኮኑ በስምከ ተነበይነ ። ዘጐ ፳፡ ፩፡ ፲፮ ። በስምህ መጻሕፍትን ተናግረን የለም ይሉኛል አስ ። በስዓም ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ ብሎ ተናግሯልና ። ወበስ ምከ አጋንንተ አውፃእነ ። ግብ. ፲፱፡ ፲፰ ። በስምህ አጋንንትን ስናወጣ አልነበርንም ይሉኛል ደቂቀ አስቂዋ ጋኔን ያወጡ ነበር ። ወበስምከ ኃይ ላተ ብዙኃ ገበርነ በስምህ ፍጹም ታምራት ስናደርግ አልነበርንም ይሉኛል ። ይሁዳ ሙት እስከ ማንሣት ደርሶ ነበርና ።

፳፫ ወይእተ ጊዜ እብሎሙ ግሙራ ኢየአምር ክሙ ረኃቁ እምኔየ ኵልክሙ እለ ትገብሩ ዓመፃ ። መዝ. ፮፡ ፱ ፤ ማቴ. ፳፭፡ ፵፩ ፤ ሉቃ. ፲፫፡ ፳፯ ።

፳፫ ያን ጊዜ ከቶ አላውቃችሁም ዓመፅን የም ትሠሩ ሁላችሁም ከኔ ራቁ እላቸዋለሁ ።
ሐተታ ፤ ፈጥርስ አላውቃችሁም አይልም ። ወስድ ኋችሁ ካድኋችሁ እላቸዋለሁ ።

፳፬ ኵሉከ ዘይሰምዕ ዘንተ ቃልየ ወይገብር ይመስል ብእሴ ጠቢበ ዘሐነጸ ቤቶ ዲበ ኰኵሕ ሉቃ. ፮፡ ፵፰ ፤ ሮሜ ፪፡ ፲፫ ፤ ያዕ. ፩፡ ፳፪ ።
፳፬ ይኸን የኔን ነገር ሰምቶ የሚሠራው ሰው ሁሉ ቤቱን በጭንጫ ላይ የሠራ ብልህ ሰውን ይመስላል ።
፳፭ ዘንሙ ዝናማት ።
፳፭ ዝናም ዘነመ ።
ወውኅዙ ወሐይዝት ።
ኀርፍ ኀረፈ ።
ወነፍሑ ነፋሳት ።
ነፋስ ነፈሰ ።
ወገፍዕዎ ለውእቱ ቤት ።
ያን ቤት እናናውጽሕ አሉት ፡ ወኢወድቀ ፡ አልተና ወጸም እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ ከጭንጫ ላይ ተሠርቷልና ሐተታ ፡ እንደምን አድርገው ይሠሩታል ቢሉ ዘይት ያፈሱበታል ይላሉ ያን እየቆፈሩ ይመ ሠርቱበታል ይጸናል ። እንድም ኵሉ ዘይሰምዕ ብስህ መልስ ። ይህን የኔን ቃል ሰምቶ የሚሠራው ሁሉ ሃይማኖቱን በበጐ ልቡና የያዘ ብልህ ሰውን ይመስላል ዘንሙ ዝናማት ከዓላውያን ነገሥታት ከዓላውያን መኳንንት የሚመጣ መከራ ነው ። ውኅዙ ወኃይ ዝት መከራ እቀበላለሁ ባለ ጊዜ ሕዋሳቱ ይፈሩበታል ነፍሑ ነፋሳት ። ቤተሰቦቹ ንጉሥ የወደደውን ዘመን የወለደውን ይዘህ አትኖርም ይሉታል ። ያን ሰው ሃይማኖትህን እናስለቅቅህ ይሉታል ። ወኢወድቀ አለቀቀም ። እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ ፡ ሃይማኖ ቱን በበጐ ልቡና ይዟልና ፡ አንድም የኔን ቃል ሰምቶ የሚሠራ ሰው ሁሉ ሃይማኖቱን ምግባሩን እንደ ኢዮ ብባለ ስውነት የያዘ ብልህ ሰውን ይመስላል ። ዘንሙ ሞተ ውሉድ ጥፍዓተ ንዋይ ነው ። ወውኅዙ ። በራሱ የሚመጣ ደዌ ነፍሑ አጋንንት በሚስቱ አድረው እስከ ማእዜኑ ትብል ኢዮብ እትዔገሥ ለእግዚአብ ሔር በየውሃት እምእይዜሰ ባርኮሁ ወሙት ብለው ታል ። ወገፍዕዎ ይህን ሰው ሃይማኖቱን ምግባሩን እናስለቅቅህ አሉት አለቀቀም ። እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ ሃይማኖቱን ምግባሩን እንደ ኢዮብ ባለ ስውነት ይዟልና ። አንድም የኔን ቃል ሰምቶ የሚ ሠራው ሰው ሁሉ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚ ኖር ብልህ ሰውን ይመስላል ነፍሑ ባሰው ይነሷል ነፍሑ ። አጋንንት በሕሊና ያወጡታል ያወርፉታል እንደ እንጦስ እንደመቃርስ ንጽሕ ጠብቁ ከሴት ርቁ እኖራለሁ ያሰኙታል ሂዶ ስመምህረ ንስሐው ይነግረዋል ቆይ ይለዋል ። ዘንሙ ዝናማት ፡ እንደ እንጦስ እንደ መቃርስ ንጽሕ ጠብቄ ከሴት ርቄ መኖር አይቻለኝም እንደ ኢዮብ እንደ አብርሃም በሕግ ጸንቼ እኖራለሁ ያሰኙታል ይህን ሂዶ ስመምህረ ንስሐው ይነግረዋል ። እሉም የሰይጣን ጾር እንደሆነ በውቆ ቆይ ይለዋል ፤ ወውኅዙ ፤ ሁሉም አይሆ ንልኝም ያሰኙታል ፤ ወገፍዕዎ እናስለቅቅሃለን ይሉ ታል አለቀቀም ። እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ ። በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ይኖራልና ። ይህ ሰው ወድቆ ተነሥቶ በሕሊናው ድል ነሥቷቸዋል ፡ ወመ ዊቶ ተንሢኦ ስፈኖሙ ስሕያዋን ወስሙታን እን ዳስው ጌታን ።

፳፮ ወኵሉ ዘይሰምዕ ዘንተ ቃልየ ወኢይገብር ይመስል ብእሴ ዓብደ ዘሐነጸ ቤቶ ዲበ ኆፃ ።

፳፮ ይህን የኔን ቃል ሰምቶ የማይሠራው ሰው ሁሉ ቤቱን በድብሽት ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመ ስላል ።

፳፯ ዘንሙ ዝናማት ፤

፳፯ ዝናም ዘነመ ፤
ወውኅዙ ወኃይዝት ፤
ጐርፍ ጐረፈ ፤
ወነፋሑ ነፋሳት ፤
ነፋስ ነፈሰ ፤
ወገፍዕዎ ለውእቱ ቤት ፤
ያን ቤት እናናዋውጽሕ አሉት ወወድቀ ፤
ወደቀ ፤

ወኮነ ድቀቱ ዓቢየ ፤
የንፍስ ነውና ዓቢየ አለ ፤

፳፰ ወሶበ ፈጸመ እግዚእ ኢየሱስ ዘንተ ነገረ ተደሙ አሕዛብ ወአንከሩ ምሕረቶ ፤

፳፰ ጌታ ይህን አስተምሮ ከፈጸመ በኋላ ሕዝቡ ትምህርቱን አደነቁ ፤

፳፱ እስመ ከመ መኰንን ይሜህሮሙ ፤ ማር ፩ ፡ ፳፪ ፡ ሉቃ ፬፡፴፪ ።

፳፱ እንደ ንጉሥ አንሰ እብለክሙ እያለ ያስተምራቸዋልና ፤ ወአኮ ከመ ጸሐፍቶሙ ከመዝ ይብሉክሙ ንጉሥ እንደሚሉ እንደ ሹማምንቱ ያይደለ አንድም እንደ አብ አንሰ እብለክሙ እያለ ያስተምራቸዋልና ፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር እንደሚሉ እንደ ዓበይተ ነቢያት ያይደለ ፤ አንድም ሠራኄ ሕግ እንደመሆኑ ያስተምራቸዋልና ፤ ከመዝ ይቤ ሙሴ ከመዝ ይቤ ሳሙኤል እንደሚሉ እንደ ደቂቀ ነቢያት ያይደለ ፤ አንድም ፈጻሚ ሕግ እንደመሆኑ ያስተምራቸዋልና ፤ ወለሊሆሙስ በአጽባዕ ቶሙጥቀ ኢይለክፍዎ ለውእቱ ጾር እንዳላቸው እንደ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ያይደለ ። አንድም ከመ ሥልጣን ቦ ይላል አብነት ላንደ ጌትነቱ በርኅራኄ ያስተምራቸዋልና ፤ እስመ ቅንየትከ ወምልኣናከ ይሬስየከ ትሠሃል ላዕለ ኵሉ እንዲል ።
ወአኮ ከመ ጸሐፍቶሙ ።
ከወርቁ የጸራውን ከግምጃው ያማረውን ከላሙ የለባውን እንደሚሉ እንደ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ያይደለ ።

በእንተ አድኅኖተ ለምጽ ።

ምዕራፍ ፰

፩ ወእንዘ ይወርድ እምደብር ተለውዎ ሰብእ ብዙኃን ።
በጌታ ከብፁዓን ጀምሮ እስከዚህ ያንድ ቀን ነው

፩ ጉባኤው ሲፈታ ብዙ ሰዎች ተከተሉት የቀሩትን አይከተሏቸውም እሱን ተከተሉት አስ ቢራቡ ይመግባቸዋል ቢታመሙ ይፈውሳቸዋል ቢሞቱ ያነሣቸዋልና ።

፪ ወናሁ መጽአ ፩ ብእሲ ዘለምጽ ቀርበ ወሰገደ ሎቱ ። ማር ፩ ፡ ፵ ሉቃ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ።

፪ ብዙኃን ካላቸው ለምጽ የያዘው አንድ ሰው ቀርቦ ሰገደለት ።

እንዘ ይብል እግዚኦ እመሰ ፈቀድከ ትክል አንጽሖትየ አቤቱ ከወደድከስ እኔን ከለምጽ ማዳን ይቻልሃል ሐተታ ለምጻምን የምታስተራኩስ ኦሪትን እሱ እንደሠራት ለማጠየቅ እንዳሳለፋትም ለማጠየቅ ለልማዱ ለምጻም አይቀርብም ነበር ።

፫ ወሰፍሐ እደዊሁ ወገሠሦ ።

፫ እጁን ዘርግቶ ዳሠሠው በሁለንተናው ሕይወት እንደሆነ ለማጠየቅ ምትሐት እንዳይደለ ለማጠየቅ ኦሪትን እንዳሳለፋት ለማጠየቅ ለልማዱ ለምጻም አይዳሰስም ነበርና ።
ወይቤሎ እፈቅድ ንጻሕ ፤
መዳንህን እወዳለሁ ዳን አለው ወነጽሐ እምልምጹ በጊዜሃ ፤ ያን ጊዜ ከለምጹ ዳነ በሐልዮ ፈውሶ በነቢብ አዳነው ። እስመ ህብተ ፈውስ ዘይከውን እምኔሁ ይቀድሞ ለንባቡ እንዲል ።

፬ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ዑቅ ኢትንግር ወኢለመኑሂ ዘሌዋ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ።

፬ ለማንም ለማን እንዳትነግር ዕወቅ አለው ። ውዳሴ ከንቱ አይሻምና የሚያምኑበት ጊዜ አልደረሰምና እስከ ትንሣኤ ድረስ ወባሕቱ ሖር አፍትን ርእሰከ ለካህን ፤
ሂደህ ራስህን ለካህን አስመርምር እንጂ ፤
ወአብእ መባዓከ በእንተ ዘንጻሕከ ፤
ከለምጽሕ ስለ ዳንህ መባሕን ስጥ እንጂ ።
በከመ አዘዘ ሙሴ ።
ሙሴ እንዳዘዘ ።
ከመ ይኩን ስምዓ ላዕሌሆሙ ባለመኑ መፈራረጃ ይሆንባቸው ዘንድ ምነው ያላመናችሁ ይሏቸዋል ምን አይተን እንመን ይላሉ ያውሳ ለምጻሙን እያዳነ መባው እየመጣላችሁ ትበሉ የነበረ ተብሎ አፍትን ርእሰከ ለካህን ማለቱ የሆነውንም ያልሆነውንም ለምጻም አዳንኩ እያለ ምኩራባችንን ቢያሳድፍብን ከሞቱ ገባንበት ባሉ ነበርና እንዳይሉ የለምጽን ነገር ከዚህ ይናገሩታል ለምጽ በብዙ ነገር ይመጣባቸዋል ባልና ሚስት የታመሙ እንደሆን ካልጋው ከምንጣፉ የጫኝ ዋጋ ቢያስቀሩ በመጫኛው ባይበቁ የጸሐፊ ዋጋ ቢያስቀሩ በመጽሐፉ የሐናጺ ዋጋ ቢያስቀሩ በሕንፃው ተወግቶ ኑሮ እሳትም ፈጅቶት ኑሮ ሲሸር ከትራቱ ይወጣል ። ፍጹም ለምፅም አለ ፤ ህንብርብር አለ ፍጹም ለምጻሙን አይለዩትም ከቀቢጸ ተስፋ ደርሱዋልና ወደ አሕዛብ ይሄዳል ፤ ብለው ህንብርብሩን ይለዩታል ከቀቢጸ ተስፋ አልደረሰምና ወደ አሕዛብ አይሄድም ብለው ፍጹም ለምጻሙን ሥራት ይሠሩበታል አትከናንብ አፍህን ሽፍን ወገብህን አትታጠቅ ጫማ አታድርግ ይሉታል ፤ ይህ የከሃዲ ምሳሌ ነው ። አትከናነብ ማለታቸው ለጊዜው ደዌው ተገልጦ እንዲታይ ነው ። ፍጻሜው ግን ልዕልና ሃይማኖት የለህም ሲሉት ነው ። አፍህን ሽፍን ማለታቸው ለጊዜው ደዌው በእስትንፋሱ ወደ ሕያዋን እንዳይናኝ ነው ፍጻሜው ግን ማስተማር አይገባህም

ሲሉት ነው ። ወንብህን አትታጠቅ ማለታቸው ለጊዜው ሰውነቱ ልህሉህ ነውና እንዳይሰማው ነው ፍጻሜው ግን ንጽሕና የለህም ሲሉት ነው ። ጫማ አታድርግ ማለታቸው ምግባረ ወንጌል የለህም ሲሉት ነው ፤ አይለዩትም አለ ከሃዲ የታወቀ ነው፡አይስ ብምና ፡ ሀንብርብር የመናፍቅ ምሳሌ ይለዩታል አለ ነኝ እያለ ይሰባልና ፡ አንድም ወእንዘ ይወርድ ብለሀ መልስ ከልዕልና ወደ ትሕትና በመጣ ጊዜ ነቢያት በግብር መሰሉት ። ወናሁ መጽአ ፤ በፍዳ የተያዘ አዳም መጥቶ ሰገደለት ። እግዚእ እመሰ ፈቀድከ እቡሉ ከወደድህስ እኔን ከፍዳ ማዳን ይቻልሃል ። ወሰፍሐ እደዊሁ ፤ እጁን ዘርግቶ ተሰቀለለት ። የማን እዴየ መጠውክዎሙ ወኮንቶሙ ጥምቀተ እንዲል ፡ እፈቅድ ንጻሕ መድኃኒትህን እወዳለሁ ዳን አለው ። ወነጽሐ እምለምጹ በጊዜሃ ያን ጊዜ ፈጥኖ ከፍዳው ዳነው፡ቅ ኢትንግር ፤ ኃጢአትህን ለማንም ለማን አትናገር አለው ፡ በአዳም መላውን መናገር ነው ። ሖር ወእፍትን ለመምህረ ንስሐህ ንገር እንጂ ፤ ወአብእ መባኣከ ፤ከፍዳህ ስለ ዳንከ ቀኖናህን ፈጽም እንጂ ፤ በከመ አዘዘ ሙሴ ፡ ቄሱ እንዳዘዘ ፡ ከመ ይኩን ስምዓ ፤ በኢተነሳሕያን መፈራረጃ ይሆንባቸው ዘንድ ።

፭ ወበዊአ ቅፍርናሆም መጽአ ኀቤሁ መስፍነ ምእት ፤ ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፩ ።

፭ ቅፍርናሆም በገባ ጊዜ የመቶ አዝማች መጣ

፮ ወይቤሎ ብቍዓኒ እግዚእ ቍልዔየ ድውይ ወሕሙም ጥቀ ።

፮ ልጄ ታሟል ፡ ደዌ ጸንቶበታል ወይሰክብ ውስተ ቤተ መፃጕዕ ፤ ከሕሙማን ቤት ተኝቷል አለው ፤ በሀገራቸው የድውያን ቤት አንድ ነው ለባለጸጋው የመጣው ምግብ ለድሃው እንዲተርፈው ደዌ ከሕሙማን ወደ ሕያዋን እንዳይተላለፍ ፤ ያል ጸናበት የጸናበትን አይቶ እግዚአብሔርን እንዲያ መሰግን ። አንድም ወይሰክብ ውስተ ቤት ብሎ ወመፃጕዕ ጥቀ ይላል ፈጽሞ ጸንቶበታል ።

፯ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ነየ አነ እመጽእ ወእፌውሶ ።

፯ እኔ መጥቼ እድንዋለሁ አለው ።

፰ ወአውሥአ ውእቱ ሀቤ ምእት ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፮

፰ የመቶ አዝማች መለሰ ።

ወይቤ እግዚእ ኢይደልወኒ ከመ እንተ ትባእ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ ።

ጥፋር ቤትየ ሲል ነው ፤ ሰጠተ ልብሱ ንፍቀ ታቦት እንዲል ፡ ሰጡጠ ልብሰ ንፋቀ ታቦተ ሲል ፡ ከኔ ቤትልትገባአይገባኝም አንተን ልቀበል አልበቃሁም አለው ። ወባሕቱ አዝዝ በቃልከ ይሕየው ቍልዔየ ልጄ ይድን ዘንድ በቃልህ አዘዝ እንጂ ነገር ግን በቃልህ አዘዝ ።

ወየሐዩ ቍልዔየ ፤
ልጄም ይድናል ።

፱ እስመ እነሂ ብእሲ መኰንን አነ ፤

፱ እኔም እንጂ እኔም አኮን እንዳቅሜ ገዥ ነኝ ።
ወብየ ሐራ ዘእኤንን ።
የምገዛቸው ጭፍሮች አሉኝ ፤ ወእብሎ ለዝ ሑር ወየሐውር ፡ ደጅ ሲጠና የሰነበተውን ሂድህ ዕረፍ እለዋለሁ ይሄዳል ።
ወለካልዑኒ ነዓ ወይመጽእ ፤
ዐርፎ የሰነበተውን መጥተህ ደጅ ጥናኝ እለዋለሁ ይመጣል ።
ወለገብርየኒ ግበር ከመዝ ወይገብር ።
ባርያየንም የቆመውን ቁረጥ የተኛውን ፍለጥ ብለው ያዘዝሁትን ሁሉ ያደርጋል ። ደዌያትስ ባንተ ዘንድ ምን ቁም ነገር ናቸው ግቡ ብትላቸው የሚገቡ ውጡ ብትላቸው የሚወጡ አይደሉምን ።

፲ ወሰሚዖ እግዚእ ኢየሱስ አንከረ ፤

፲ ጌታ ይህን ሰምቶ አደነቀ ። ሦስት ነገር አግኝቶ ያደንቅለታል ሃይማኖት ፡ ጥበብ ፡ ትሕትና ፤ ሃይማኖት ያድንልኛል ብሎ መምጣት ፤ ጥበብ ምሳሌ መስሎ መናገር ፤ ትሕትና ኢይደልወኒ አይገባኝም ማለት ነው ።
ወይቤሎሙ ለእለ ይተልውዎ አማን እብለከሙ ፤ ኢረከብኩ ከመዝ ዘይትአመን በውስተ ኵሉ እስራኤል ።
ለተከተሉት በእስራኤል ዘንድ እንዲህ ያለ እማኒ አላገኘሁም ብየ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ። አንድም ወበዊአ ብፅህ መልስ ። ከልዕልና ወደ ትሕትና በመጣ ጊዜ የሁሉ መገናኛ አዳም መጣ ። ቍልዔየ ድውይ፡ አቤቱ ነፍሴ በፍዳ ተይዛለች አለው ። ወሕሙም ጥቀ ፍዳ ጸንቶባታል ፡ ወይሰክብ ውስተ ቤተ መፃጉዕ ፡ በኃጥአን ቤት በሲኦል በፍዳ ተይዛለች ። ነየ አነ እመጽእ ወእፌውሶ ። በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ያለውን መናገር ነው ። ኢይደልወኒ አዳም አድነኝ አለ እንጂ ሰው ሁንልኝ አለማለቱን መናገር ነው ። እስመ እነሂ ፡ እኔም እንጂ እኔም እኮን እንዳቅሜ ገዥ ነኝ። ወብየ ሐራ የማወጣቸው የማገባቸው ሕሊናት አሉኝ ። ወእብሎ ለዝ ሑር ከፉውን ሕሊና ውጣ ብለው ይወጣል ወለካልኡኒ ነዓ ወይመጽእ ። በጐውን ሕሊና ግባ ብለው ይገባል ። ወለገብርየኒ ሥጋዬን ለነፍሴ ተገዛ ብለው ይገዛል ። አጋንንትስ ባንተ ዘንድ ምን ቁም ነገር ናቸው ። ግቡ ብትላቸው የሚገቡ ውጡ ብትላቸው የሚወጡ አይደሉምን አለው ። ወሰሚዖ አይለወጥም ።

፲፩ ወባሕቱ እብለከሙ ብዙኃን ይመጽኡ እምሥራቅ ወእምዕራብ ወይረፍቁ ውስተ ሕፅነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ በመንግሥተ ሰማያት ።

ይህ ሰው ትውልዱ ከእስራኤል ነው ያሉ እንደሆነ ፤ ይህስ የተገኘ ከኛ አይደለም እንዳይሉት ።

፲፩ ነገር ግን ካራቱ ማዕዘን የሚያምኑብኝ ብዙ አሉ ። ይህ ሰው ትውልዱ ከአሕዛብ ነው ያሉ እንደሆነ አንድ ሰው ቢያምንበት እንዲህ ያደንቃል እንዳይሉት ሌሎችም ካራቱ ማዕዘን መጥተው የሚያምኑብኝ አሉ ፤ ወይረፍቁ ፥ በምስቱ ሕፅን ይቀመጣሉ ማለት በአብርሃም በይስሐቅ ፥ በያዕቆብ ፥ ቃል ኪዳን በምትወረስ በመንግሥተ ሰማይ ይኖራሉ ።

፲፪ ወለውሉደ መንግሥትሰ ያወፅእዎሙ ውስተ ጸናፌ ጽልመት ሚልክ ፩፥፲፩ ።

፲፪ ይገባናል የሚሉ እስራኤልን ግን ከመንግሥተ ሰማይ አፍአ ወደ ገሃነም ያወጣቸዋል ።
ኀበ ሀሎ ብካይ ወሐቀየ ስነን ፥
ልቅሶ ጥርስ ቁርጥማት ወዳለበት

፲፫ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ለውእቱ ኀቤ ምእት ሑርኬ ይኩንከ በከመ ተአመንከ ።
፲፫ ጌታም የመቶውን አዝማች ሂድ እንዳመንህ ይደረግልህ አለው ።
ወሐደወ ወልዱ በይእቲ ሰዓት ልጁም ያንጊዜ ፈጥኖ ዳነ ። የአዳም ነፍሱ ከፍዳ ዳነች ።
ወገቢእ መስፍን ውስተ ቤቱ ረከቦ ለወልዱ ሕያዎ ። ወደቤቱ በተመለሰ ጊዜ ሐደዎድኖ ሕያወ የዳነ ሁኖ በዘሐይወ በዳነ ገንዘብ አገኘው ።
በእንተ ሐማተ ጴጥሮስ ።
፲፬ ወበዊአ ቤቶ ለጴጥሮስ ረከባ ለሐማተ ጴጥሮስ እንዘ ትሰክብ ወትፈጽን ።
፲፬ ከጴጥሮስ ቤት በገባ ጊዜ ሐማተ ጴጥሮስን ሆድ ዝማ ታማ ተኝታ አገኛት ።
፲፭ ወአኃዛ እዴሃ ወገሠሣ ።
፲፭ እጁዋን ይዞ ዳሰሳት ፡ ወኃደጋ ፈጸንታ ። ሆድ ዝማዋ ተዋት ። ወተንሥአት ወተልእከቶሙ ። ተነሥታ አገለገለቻቸው ። መፈትፈት ማሳለፍ አይደለም ለጊዜው የሚበሉትን እያዘጋጀች አቀረበችላቸው ፍጻሜው ግን ከ፴፮ቱ ቅዱሳት አንስት ገብታ ተቈጠረች ፤ አንድም ወበዊአ ብስሀ መልስ እሥራኤልን በመከበባቸው ጴጥሮስ አባቸው ጌታ ወደ እሥራኤል በመምርነት በገባ ጊዜ ረከባ ለሐማተ ጴጥሮስ ፤ ኦሪትን ስብ ስታጤስ ደም ስታፈስ አገኛት ወአኃዛ እዴሃ ፲ቱ ቃላትን ባሉት አጽንቶ አሳሰፋት ። ወኃደጋ በአሪት ሥራት ደም ማፍሰስ ስብ ማጤስ ቀረ ። ወምሴተ ከዊኖ አምጽኡ ኀቤሁ

፲፮ ብዙኃነ እለ አጋንንት ማር ፡ ፩ ፥ ፴፪ ።

፲፮ ወምሴተ ከዊኖ ወሶበ መስየ ይላል ። ሲመሽ በመሸ ጊዜ ብዙ አጋንንት ያደሩባቸው ሰዎች ይዘውመጡ ። ፈውሱ ከዓቀብተ ሥራይ ልዩ ነውና እነዚያ በዚህ ዕለት እንጂ በዚህ ዕለት በዚህ ሰዓት እንጂ በዚህ ሰዓት አይቻለንም ይላሉ ፥ እሱ ግን በመጡበት ሰዓት ሁሉ ያድናቸዋልና ።
ወአውጽኦሙ በቃሉ ።
ፃኡ መናፍስት ርኩሳን ብሎ አወጣቸው ።
ወፈወሰ ኵሎ ሕሙማን ።
ሕሙማኑን አዳነ ። ከመ ይትፈጸም ቃል

፲፯ ኢሳይያስ ነቢይ ዘይቤ ውእቱ ነሥአ ደዌነ ወጾረ ሕማመነ ኢሳ ፡ ፶፫ ፥ ፬፥፭፥ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ።

፲፯ ደዌያችንን ተሸከመ ማለት ኢሳይያስ ደዌ ሥጋችንን በታምራት ደዌ ነፍሳችንን በትምህርት አራቀልን ብሎ የተናገረው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ድውያነ ሥጋን በተአምራት ድውያነ ነፍስን በትምህርት አዳነ፤ አንድም ድውያነ ነፍስን በትምህርት አዳነ ብሎ ኢሳይያስ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ድውያነ ሥጋን በታምራት አዳነ ሞተ ሥጋው ለሞተ ነፍስ ምልክት እንደሆነ ድኅነተ ሥጋው ለድኅነተ ነፍስ ምልክት ነውና አንድም እስከ አፅርዓ ወአሰሰለ ይላል አብነት ደዌ ነፍሳችንን በመስቀል ተሰቅሎ እስኪያርቅልን ድረስ ደዌ ሥጋችንን በታምራት አራቀልን ብሎ ኢሳይያስ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ፈወሰ ድውያንን አዳነ ። አንድም ነቢይ ነሥአ ደዌነ ወጾረ ሕማመነ እንዳለ ፥ ወንጌላዊ ነሥአ ደዌነ ወጾረ ሕማመነ ፤ ደዌያችንን ነሣ አለ ታሪክ ከራድዮን የሚባል ጸዓዳ ዖፍ አለ ይዘው ከቤተ መንግሥት ወስደው ያኖሩታል ሰው ሲታመም ወስደው ያቀርቡታል የሚሞት የሆነ እንደሆነ አያየውም ፊቱን ይመልስበታል የሚድን የሆነ እንደሆነ ያየዋል ቀርቦ አፉን ከፉ አድርጎ እስትንፋሱን ይቀበለዋል በእስትንፋስ ምክንያት ደዌ ወደሱ ይመለሳል ነጭ የነበረ ይጠቁራል ብርድ ብርድ ይለዋል ዋዕይ ሲሻ ወደ አየር ይወጣል ዋዕይ ሲሰማው ከባሕር ይገባል ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በባሕር ኑሮ የቀደመ ጠጕሩን መልጦ ታድሶ ይወጣል ፤ ከራድዮን የጌታ ምሳሌ ጸዓዳ እንደሆነ ጸዓዳ በመለኮቱ ይሰዋልና ድውይ የአዳም ምሳሌ እንደ ማየት በዓይነ ምሕረት አይቶታልና ቀርቦ እስትንፋሱን እንደመቀበል ባሕርዩንባሕርይ አድርጎለታል በእስትንፋስ ምክንያት ደዌ ወደሱ እንደ ተመለሰ ፤ በአዳም የተፈረደውን መከራ ጌታ ለመቀበሉ ምሳሌ ። ወቦእ እግዚእነውስተ ኵሉጸዋተወመከራ እንተ ባቲ አመከረነ ጸላዒ እንዲል ፥ ወደዓየር ወደ አየር እንደመውጣት በመስቀል ተሰቅሏልከባሕርእንደመግባትወደመቃብር ወርዷል ፫ ሌሊት ፫ መዓልት በከርሠ ባሕር ኑሮ የቀደመ ጠጕሩን ትቶ እንደመነሣት ፫ መዓልት ፫ ሌሊት በከርሠ መቃብር ኑሮ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ አንድ ወገን ሁኖ ለመነሣቱ ምሳሌ ፥ ኅደገ ንዴተ ህላዌ ተመይጠ ወገብአ ኀበ ስብሐቲሁ ወክብሩ እንዲል

በእንተ ዘከመ ይደሉ
ተሊዎተ እግዚእ ኢየሱስ ።
ወሶበ ርእየ ብዙኃነ ሰብአ ዘተለውዎ አዘዘ ይሑሩ ማዕዶተ ባሕር የተከተሉትን ብዙ ሰዎች ባየ ጊዜ ባሕሩን ተሻግራችሁ ቆዩኝ አላቸው ። አሁን ብሔረ ጌርጌሴኖን ገባ ብሎ እንዲያመጣው ፤ ሐተታ ፤ እስራኤል አሕዛብን ይጸየፏቸዋልና እንዳይጸየፉ ጌታ ኢያሱን አሕዛብን ፈጽመህ አታጥፏቸው ብሎታል ። ከመ ኢትኩን ምድር አጸ ። ምድረ በዳ እንዳትሆን እስራኤል እየቀደሙ እየበዙ ሊወርሷት ቢታበዩ ሊቀጣቸው ጸር ሊያስተምሯቸው እንደዚህም ሁሉ ጌታ አጋንንትን ፈጽሞ አላጠፋቸውም የምእመናን ልቡና ከትሩፋት ባዶ እንዳይሆን ቢታበዩ ሊያዋርዱዋቸው ጸር ሊያስተምሯቸው ።

፲፰ ወመጽአ ኀቤሁ አሐዱ ጸሐፊ

፲፰ ጸሐፊ ማለት ዐዋቂ ነኝ የሚል ሰው ወደሱ መጣ ።
ወይቤሎ ሊቅ እትሉከኑ ኀበ ሖርከ ።
መምህር ልደርልህ አለው ።

፲፱ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ለቈናጽልኒ ግበብ ቦሙ ።

፲፱ ለቀበሮች ፍርክታ አላቸው ።
ወለአዕዋፈ ሰማይኒ ምጽላል ቦሙ
ለአዕዋፍም ማረፊያ መኖሪያ ዛፍ አላቸው ።

፳ ወለወልደ ዕጓለ እመሕያውሰ ወአልቦቱ ኀበ ያሰምክ ርእሶ ። ሉቃ ፱ ፤ ፶፰ ።

፳ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ለኔ ግን ራሴን የማስጠጋበት ቦታ የለኝም ፤ ለመኳንንቱ ለካህናቱ አደርላቸው እንጂ ለኔ ለምን ታደርልኛለህ አለው ። ቆናጽል አላቸው መኳንንትን ቄንጸልን ተመያኒ ይለዋል ቴንኮለኛ ነው ወያወፅእ ፊላዮ እንዲል ፤ ከፉ መዓዛ አለው ያን አውጥቶ የሞተ መስሎ ከጉድጓዱ አፍ ወጥቶ ይተኛል ። ተሐዋስያን ሲሸታቸው የሞተ መስሏቸው ሲበሉ ይቀርባሉ እያነቀ ከጉድጓድ ይዞ ገብቶ ይመገባል ። መኳንንትም በተሾሙበት አገር በኛ ጊዜ ርስትህን ጉልትህን ካላስመለስህ በማን ጊዜ ልታስመልስ ነው ብለው ይገጥሙታል ቢረታ ዳኝነት ቢረታ መማለጃ ይበሉታልና ። ካህናትን አዕዋፍ አላቸው ለአዕዋፍ ዘር መከር እንደሌላቸው ለካህናትም ዘር መከር የላቸውምና ፤ አንድም በቍንጽል በዖፍ ለተመሰለ ለገንዘብ አንተ ማደሪያ አለኸው ። ቍንጽል አለው ይተነኩሉበታልና ። ዖፍ አለው ፈጥኖ ይጠፋልና ። ወልደ ዕጓለ እመሕያውሰ ፤ ልደርልህ ማለት እንጂ አደርብኝ ማለት ነው የገንዘብ ማደሪያ ሁነህ በየት ልደርብህ አለው ። አንድም ቍንጽል ዖፍ ለተባለ ለዲያብሎስ ማደሪያ አንተ አለኸው የተመቸ ተንኮለኛ ነውና ። ዖፍ ፈጥኖ ያስታልና በውሳጤ ቤትከ ኢትርግም ብዕላነ እስመ ዖፈ ሰማይ ያወፅኦ ለነገርከ እንዲል ። ወልደ ዕጓለ እመሕያውሰ የዲያብሎስ ማደሪያ ሁነህ ሳለህ በየት ልደርብህ አላደርብህም አለው ። አንድም ለቍንጽል ለዖፍ ላንተ ማደሪያ ገሃነም አለህ ፤ እኔ ግን አላደርብህም ። ቍንጽል አለው ጥንቆላ መስሎት ተምሬ በታምራቱ እበላበታለሁ ብሎ በተንኮል መጥቷልና ፤ ዖፍ አለው በጥቂት ቀን ነጥቄ እሄዳለሁ ብሎ መጥቷልና ፤ አንድም ለቆናጽል ለአይሁድ ማደሪያ ገሃነም አላቸው ። በአዕዋፍ በሐዋርያት እኔ አድርባቸዋለሁ በአይሁድ ግን አላድርባቸውም ። ምጽላል ባለው አበኳር የሚል አብነት ይገኛል የጭቃ ቤት የምትሠራ ዖፍ አለችና ።

፳፩ ወይቤሎ ካልእ እምአርዳኢሁ እግዚእ አብሐኒ እቅድም ወእሑር ወእቅብር ለአቡየ ።

፳፩ ከሕዝቡ አንዱ አሰናብተኝ አስቀድሜ ሂጄ አባቴን ልቅበር አለው ። ከጉባኤው ከዋለ ሁሉንም ደቀ መዝሙር ማለት ልማድ ነውና እንዲህ አለ እንጂ ከሕዝቡ አንዱ ነው ። ሙቷል ቢሉ ልቅበረው አልሞተም ቢሉ ልርዳው አለው ፤

፳፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ እንተሰ ትልወኒ

፳፪ አንተስ ተከተለኝ አለው ። ለጊዜው በእግር ተከተለኝ ፍጻሜው በግብር ምሰለኝ አለው ። ወኅድጎሙ ለምውታን ይቅብሩ ምውታኒሆሙ ። ሙተዋል ቢሉ ሙታን እናት አባትህን ሙታን ሕሊና ዘመዶቻቸው ይቅበሯቸው አንድም አልሞቱም ቢሉ ሙታን ሕሊና እናት አባትህን ሙታን ሕሊና ዘመዶቻቸው ይርዷቸው ያጥቧቸው ፤ አንድም ሙታን ሕሊና እናት አባትህን ምውት ገንዘባቸው ይርዳቸው ያጥባቸው ።

በከመ አኅደኖ ለባሕር

፳፫ ወዓረገ ውስተ ሐመር ተለውዎ አርዳኢሁ ። ማር ፬ ፤ ፴፮ ።

፳፫ ከመርከብ በወጣ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት ።

፳፬ ወናሁ ዓቢይ ድልቅልቅ ኮነ በውስተ ባሕር ።

፳፬ ባሕሩ ተናወጸ ።
እስከ ሶበ ይደፍኖ ለሐመር ማዕበለ ባሕር ።
ማዕበሉ መርከቡን እስጥመዋለሁ እስኪል ድረስ
ወውእቱሰ ይነውም ።
እሱ ግን ተኝቶ ነበር ኖመ ከመ ውሉደ ሥጋ እንዲል ።

፳፭ ወቀርቡ አርዳኢሁ ወአንቅሕዎ ፤

፳፭ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው ቀሰቀሱት ፤ ወይቤልዎ እግዚእ አድኅነነ ከመ ኢንሙት ። አቤቱ ከስጥመት አድነን አሉት ።

፳፮ ወይቤሎሙ ምንት ያፈርሃክሙ አሕጹጻነ ሃይማኖት ።

፳፮ እናንት ሃይማኖት የሌላችሁ ምን ያስፈራችኋል ከሱ ጋራ ሳለን ጥፋት አያገኘንም በሱ ስም አምነን እንድናለን እትሉም አላቸው ።
ወተንሥአ ገሠጾሙ ለነፋሳትኒ ወለማዕበለ ባሕር።
ተንሥቶ ነፋሳትን ማዕበለ ባሕርን ገሠጻቸው ።
ወኮነ ዓቢይ ዛኀን ።
ታላቅ ጸጥታ ተደረገ ማለት ጸጥ አለ ።

፳፯ ወአንከሩ ሰብእ ።
፳፯ ሕዝቡ አደነቁ ።

ወይቤሉ መኑ እንጋ ውእቱ ዝንቱ ዘይትኤዘዙ ሎቱ ባሕርኒ ወነፋሳትኒ ።
ባሕር ነፋሳት የሚታዘዙለት ይህ ማነው አሉ ።
አንድም ወዓሪገ ብለህ መልስ አሪትን በሥራ ጊዜ ነቢያት ፣ ወንጌልን በሥራ ጊዜ ሐዋርያት በግብር መሰሉት ።
ወናሁ ዓቢይ ድልቅልቅ ኮነ በውስተ ባሕር ።
በሰውነታቸው መከራ ጸናባቸው ። እስከ ሶበ ይደፍኖ ለሐመር ። ሕጋቸው አሪትን ሕጋቸው ወንጌልን አስተዋቸዋለሁ እስኪል ድረስ ፣ ወእቱሰ ይነውም ትዕግሥቱን መናገር ነው ። ቀርቡ ወአንቅሕዎ ፣ አቤቱ ከመከራ አድነን ብለው ለመኑት ፣ ምንት ያፈርሃክሙ እኁጹጻነ ሃይማኖት፣መከራ ብትቀበሉ ክብር ይበዛላችኋል እንጂ ምን ያደርጋችኋል ምን ያስፈራችኋል አላቸው ። ወተንሥአ ገሠጾሙ ፣ ከትዕግሥቱ ወጥቶ መከራውን አራቀላቸው ወኮነ ዓቢይ ዛኀን ። መከራው ራቀላቸው አንድም ወዓሪገ ፣ ታባሕትዎ በያዘ ጊዜ ባሕታውያን ፣ ወደ መስቀል በወጣ ጊዜ ሰማዕታት በግብር መሰሉት በሰውነታቸው መከራ ጸናባቸው ፣ ገድላቸውን እስኪያስተዋቸው ድረስ ፣ ትዕግሥቱን መናገር ነው ። ለመኑት እናንት ሃይማኖት የሌላችሁ ምን ያስፈልራችኋል ፣ መከራ ክብር ያበዛላችኋል እንጅ ምን ያደርጋችኋል አላቸው ከትዕግሥቱ ወጥቶ ለሰማዕታት ነበልባል እብርዶ አንበሳ አሰግዶ ለባሕታውያን ቀራ እንዲታለብላቸው ዛፍ እንዲያፈራላቸው አንድርጎ ረዳቸው ፤ መከራው ቀረ ።

በእንተ አጋንንት
ዘብሔረ ጌርጌኖን ።

፳፰ ወበጺሖ ማዕዶተ ጌርጌሴኖን ተቀበልዎ ፪ቱ እለ አጋንንት ወፂአሙ እመቃብራት ። ማር ፭ ፥ ፩ ፥ ሉቃ ፰ ፥ ፳፮ ፥

፳፰ ጌርጌሴኖን በደረሰ ጊዜ አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች ከመቃብር ወጥተው ተቀበሉት ። ባንዱ ሽህ ባንዱ ሽህ አድረውባቸዋል ሰው ከሚቀብርበት ላም ከሚታረድበት አጅ ከሚጣልበት መናገር ስጋኔን ሊማዱ ነውና ፣ አንድም ነፍስ በሕያው አድራ መቃብሯን ትጠብቃለች የሚሉ አሉና ለማስመሰል ፣ አንድም የምውት ነፍስ በሕያው አድራ የዘመዶችዋን ጠላት ታጠፋለች የሚሉ አሉና ያን ለማስመሰል ይህን ይዘው የዘመዶቻችን ነፍስማ ጠላቶቻችንን የምታጠፋልን ከሆነ የልጆቻችን ነፍስማ እንደምን ታጠፋልን ብለው ልጆቻቸውን አርደው የፈጁ ብዙ ናቸው ። አንድም በሕያዋኑ አድረውባቸዋል በምውታኑ አድረን እንኖራለን ፣ ዲያብሎስ እግዚአ ሕያዋን ወሙታን ነኝ ሲል ፣ ወወፂአሙ እመቃብራት አለ ።
ወእኩያን ጥቀ ወኢያበውሑ መኑሂ ይኅልፍ እንተ ይእቲ ፍኖት ።
እጅግ ክፉ ናቸው ማንንም ማን በዚያች መንገድ ሊሄድ አያስናብቱትም ነበር ፣ አንድም ኢያበውሑ መኑሂ ይላል በዚያች መንገድ ይሄድ ዘንድ ማንንም አያሰናብቱም ነበር ።

፳፱ ወናሁ ጸርሑ እንዘ ይብሉ ምንት ብነ ምስሌከ ኢየሱስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው

፳፱ የሕያው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ካንተ ጋራ ምን ጸብ አለን ፣ አንድም ካንተ ጋራ የምንቃወምበት ምን ኃይል ምን ሥልጣን አለን ብለው አሰምተው ተናገሩ ።
መጻእከኑ ዝየኒ ትስድደነ ፣
ከዚህም አስወጥተህ ልትሰድደን መጣህን ሐተታ ዝየኒ ማለታቸው ቀድሞ ከኢየሩሳሌም ኋላ ከሄሮድስ ከተማ አስወጥቶ ሰዷቸው ነበርና ፣ ወዘእንበለ ይብጻሕ ጊዜሁ ትሣቅየነ ፣ ፍዳ የምንቀበልበት ጊዜ ሳይደርስ ሥቃይ ልታጸናብን መጣህን አሉት ፣ ጊዜው ዕለተ ዓርብ ዕለተ ምጽአት ነው ፣

፴ ወቦ ህየ መራዕየ አሕርው ይትረአዩ ርሑቀ እምኔሆሙ ማር ፭ ፣ ፲፩ ፣ ሉቃ ፣ ፰ ፣ ፴፪

፴ የእሪያ መንጋ ከሳቸው ርቀው ተሰማርተው ነበር ።

፴፩ ወአስተብቍዕዎ እሙንቱ አጋንንት ፤
፴፩ አጋንንት ማለዱት ።
ወይቤልዎ እመሰ ታወፅአነ ፈንወነ ዲበ መራዕየ አሕርው ፤ ከሰዎቹስ ካወጣኸን በአሕርው እናድርባቸው ዘንድ እዘዘን አሰናብተን አሉት ፤ ሐተታ ፣ ሰንኳን አእምሮ ንባብ ባለው ሰው አእምሮ ንባብ በሌላቸው በአሕርው ያለሱ ፈቃድ ማደር እንዳይቻላቸው ለማጠየቅ ።
፴፪ ወይቤሎሙ ሑሩ ።

፴፪ ሂዱችሁ እደሩባቸው አላቸው እኮ ከመ ይግበር ስእለቶሙ ብሎታል ሊቁ ፣ አሁን ጌታን ስለእለተ አጋንንት ደስ አሰኝቶት አይደለም በተንኮል መጥተዋል አሕዛብ እሪያውን እንደ ከብት እያረቡ ሥጋውን ይበሉታል ፣ ወተቱን ይጠጡታልና

እኒህን ያጠፋንባቸው እኛ ደሆን እሱን ይማሉልናል ብለው መጥተዋል ። ጌታም ሒዱ አደሩባቸው አላቸው እኒህ ኀደሉ ወድቀው ባሕር ጠልቀው ቢያልቁ ምድር ተከፍቶ የሚያስጥማቸው ነውና ፣ በዚያው ሥራውን ለመሥራት ሂዱ እደሩባቸው አለ ።

ወወፂኦሙ ሖሩ ወቦኡ ውስተ አሕርው ከሰዎች ወጥተው በአሕርው አደሩ ። ወሮጹ ኩሉ መራዕየ አኅርው ወጸድፉ ውስተ ባሕር ወሞቱ ውስተ ማይ ጥቂት የደመ ነፍስ አእምሮ ነበራቸው ያችኑ አጥተዋት ኀደሉ ወድቀው ከባሕር ጠልቀው አለቀዋል ። አሕርው የአይሁድ አጋንንት በአይሁድ ያደሩ የአጋንንት ምሳሌ ሠረውንም አሠረውንም አንድ አድርጎ ገሃነም እንዲያወርድ ለማጠየቅ ፣ አንተ ወጣዖታቲከ ኅቡረ ትወርዱ ውስተ ገሃነም እንዲል ።

፴፫ ወጐዩ ኖሎት ወአተው ሀገረ ወዜነው ኵሎ ዘኮነ ።

፴፫ ጠባቆች ሸሽተው አገር ገብተው የአሕርውን ስጥመት ተናገሩ ወዘእለ አጋንንትኒ ፣ የአጋንንትንም ጥፋት የሰዎችንም ድኅነት ተናገሩ ።

፴፬ ወናሁ ወፅአ ኵሉ እለ ውስተ ሀገር ይትቀበልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፴፬ በሀገር ያሉ ሰዎች ሁሉ ሊቀበሉት ወጡ ወሶበ ርእይዎ አስተብቍዕዎ ይኅልፍ እምደወሎሙ ባዩት ጊዜ ካገራችን እለፍልን ብለው ለመኑት ። ንባብ አእምሮ በሌላቸው በአሕርው እንዲህ አድርጎ የፈረደ ንባብ አእምሮ ያለን የኛን ኃጢአትማ መርምሮ ዐውቆ እንደምን ይፈርድብን ብለው ።

በእንተ መጻጕዕ ።

ምዕራፍ ፱ ።

፩ ወዓርገ ውስተ ሐመር ዓደወ ወበጽሐ ሀገሮ ፤ በመርከብ ተጭኖ ባሕሩን ተሻግሮ ወደ አገሩ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ ።

፪ ወአምጽኡ ኀቤሁ ድውየ መፃጕዓ እንዘ ይጸውርዎ በዓራት ማር ፪ ፡ ፫ ፡ ሉቃ ፡ ፭ ፡ ፲፰ ።

፪ ደዌ የጸናበት አንድ ሰው ባልጋ ተሸክመው ወደሱ መጡ ። ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ሃይማኖቶሙ ይቤሎ ለውእቱ መፃጕዕ ተአመን ወልድየ ያድኑልናል ብለው መምጣታቸውን ፣ አንድም ሃይማኖቶ ይላል ያድነኛል ብሎ መምጣቱን አይቶ ልጄ ሃይማኖትህ አድኖሃልና በሃይማኖትህ ጽና ወተኅደግ ለከ ኃጢአትከ ። ኃጢአትህም ተሰርዮልሃል አለው ።

፫ ወናሁ አሐ እምውስተ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ይቤሉ ዝሰ ይፀርፍ ።

፫ ከጸሐፍት ከፈሪሳውያን ወገን የሚሆኑ ይህስ ይሳደባል አሉ ፤

፬ ወአእሚሮ እግዚእ ኢየሱስ ሐሊናሆሙ ወይቤሎሙ ለምንት ትሔልዩ እኩየ በአልባቢክሙ ።

፬ ጌታ እንዲህ ማለታቸውን ዐውቆ በልቡናችሁ ክፉ ነገርን ለምን ታስባላችሁ አላቸው ።

፭ ምንት ይቀልል እምብሂለ ተኅደግ ለከ ወእምብሂለ ተንሥእ ወንሣእ ዓራተከ ወሑር ፤

፭ ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ከማለትና ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል ከማለት ማናቸው ይቀላል አላቸው ።

፮ ከመ ታእምሩ ከመ ብውሕ ሎቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ይኅድግ ኃጢአተ በዲበ ምድር ።

፮ ለሰው ልጅ ለክርስቶስ በዚህ ዓለም ኃጢአት ማስተስረይ እንዲቻለው ታውቁ ዘንድ ፣ ሐተታ ፣ ኃጢአት ከማስተስረይ ድውይ መፈወሱን ማብለጡ ነው ፤ ሁሉስ የጌትነት ሥራ አይደለም ቢሉ ኃጢአት ሲሰረይ አይታይም ድውይ ሲፈውስ ይታያልና ፣ ሰውም ካላየው ያየውን ማድነቅ ልማድ ነውና ፣ ሰው በሚያደንቀው ተናገረ ። አንድም ኃጢአት ተሰረየልህ ከማለትና ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ከማለት ማን ይቀላል ፣ ድውይ ሲፈውስ አይታችሁ ኃጢአት ያስተሰርያል አትሉም አላቸው ሞተ ሥጋ ለሞተ ነፍስ ምልክት እንደሆነ ድኅነተ ሥጋው ለድኅነተ ነፍስ ምልክት ነውና ።

ወእምዝ ይቤሎ ለውእቱ መፃጕዕ ተንሥእ ወንሣእ ዓራተከ ወሑር ቤተከ ።

ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ አለው ፣ ሐተታ ፣ ተረፈ ደዌ የለበትምና ፈውሱ ከዓቀብተ ሥራይ ልዩ ነውና እነዚያ እዳንን ካሉ በኋላ እህል ይቅመስ ይዋል ይደር ይጽናና ይላሉ ፤ እሱ ግን ተረፈ ደዌ የለበትምና ። አንድም እነዚያ እዳን ብለው የሚጠጣበት ጽዋው የሚተኛበት አልጋው ምንጣፉ ይገባልና ይላሉ እሱ ግን ይህ ሁሉ የለበትምና ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ
፯ አለው ። ወተንሢአ ነሥአ ዓራቶ ወሖረ ቤቶ ፤
፯ ተነሥቶ አልጋውን ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሄደ።
፰ ወርእዮሙ ሕዝብ አንከሩ
፰ ሕዝቡም አይተው አደነቁ ፤ ወአእኰትዎ ለእግዚአብሔር ዘወሀበ ዘከመዝ ሥልጣነ ለሰብእ ለሰው እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠው ማለት አላመኑም ቢሉ እንዲህ ያለ ነቢይ ያሥነሣልን ብለው፣ አምነዋል ቢሉ ለራሱ ድኅነት ይሻ የነበረ ሥጋን ከባ

ሕርይ ልጅህ ጋራ አዋሕደሀ ለሌላው ድኅነትን እንዲያድል ያደረግኸው ብለው እግዚአሐርን አመሰገኑት ።

ዘከሙ ተጸውዓ ማቴዎስ ።

፱ ወኃሊፎ እግዚእ ኢየሱስ እምህየ ረከበ ብእሴ እንዘ ይነብር ውስተ ምጽባሕ ዘስሙ ማቴዎስ ፤ ማር ፪ ፡ ፲፬ ፡ ሉቃ ፡ ፭ ፡ ፳፯

፱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚያ አልፎ ሲሄድ ማቴዎስ የሚባል ሰው ከሚያስገብርበት ቦታ ተቀምጦ አገኘ ፤ ሐተታ ፡ ሲያስገብር አላስም የሰው ገንዘብ ይዞ ሄደ ብለው ምክንያት እንዳያደርጉበት ።

ወይቤሎ ትልወኒ ።

ተከተለኝ ማለት ስጊዜው በእግር ፍጻሜው ግን በግብር ምሰለኝ አለው እንዲሻው ከፍጹምነት እንዲደርስ ዐውቆ ።

ወተንሢአ ተለዎ ።

ተነሥቶ ተከተለው ማለት ስጊዜው በእግር ፍጻሜው በግብር መሰለው ።

በእንተ ዘከመ ይደልዎሙ

ለክርስቲያን ጾዊመ ፤

፲ ወእንዘ ይረፍቅ ውስተ ቤት ናሁ መጽኡ ብዙኃን ኃጥአን መጸብሓን ።

፲ ከቤት ገብቶ ሲበላ ብዙ ኃጥአን መጸብሓን መጡ ።

ወረፈቁ ምስለ እግዚእ ኢየሱስ ወአርዳኢሁ ። ከደቀ መዛሙርቱም ከሱም ጋራ ተቀምጠው በሉ ። እንዲያው አይደለም ተከተለኝ ካልኸኝስ ከቤት ገብተህ ምሳ ብላልኝ ብሎታል ፤ የቤቴን ትዳር ያየእንደሆነ አከብሮ ያኖረኛል ብሎ አሁን ዛሬ ለጌታ የሚያድር ሰው ፈረሱን በቅሎውን ሎሌውን ገረዱን አብዝቶ እንዲታይ ። አንድም ፡ ትእምርተ ምናኔ ነው ፩ ፡ ነገ ፡ ፱ ፡ ፱ ። ኤልሳዕ ፲ ፡ ሁለት ጥንድ በሬ አስጠምዶ ሲያሳርስ ኤልያስ ሐሜለቱን ከራሱ ላይ ጥሎ ተከተለኝ አለው ። አባቴ ተከተለኝ ካልኸኝስ ቆየኝ አንድ ጊዜ ብሎ ፲፪ቱን ጥንድ በሬ አርዶ ለነዳያን አብልቶ ተከትሎታልና በዚያ ልማድ ።

፲፩ ወርእዮሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ይቤልዎሙ ለአርዳኢሁ ለምንት ይበልዕ ሊቅክሙ ምስለ ኃጥአን ወመጸብሐን ።

፲፩ ጸሐፍት ፈሪሳውያን አይተው መምህራችሁ ከኃጥአን ከመጸብሐን ጋራ ለምን ይባላል አሏቸው

፲፪ ወሰሚዖ እግዚእ ይቤሎሙ ሕሙማን ይፈቅድዎ ለዓቃቤ ሥራይ ።

፲፪ ጌታም በሰማ ጊዜ ባለመድኃኒትን የታመሙ ሰዎች ይሹታል ። ሐተታ ያበጠውን ሊፈርጥላቸው የጎረበጠውን ሊልጥላቸው ፤

ወአኮ ጥዑያን ።

ጤነኞች ግን አይሹትም ። አንድም ዓቃቤ ሥራይ ዘነፍስ እኔን ሕሙማን ነን የሚሉ ኃጥአን መጸብሐን ይሹኛል ደኅነኞች ነን የምትሉ እናንተ ግን አትሹኝም ።

፲፫ ሑሩ ወአእምሩ ምንት ውእቱ ዘይቤ ምጽዋተ አበድር እመሥዋዕት ። ሆሴ ፡ ፮ ፡ ፮ ። ማቴ ፡ ፲፪ ፯ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።

፲፫ ሑሩ በእግረ ሕሊና ነው ምጽዋተ አበድር እመሥዋዕት ያለው ምንም እንደሆነ መርምራችሁ ዕወቁ ማለት እኒህን መጸየፍ መሥዋዕት እኒህን አለመጸየፍ ምጽዋት እንደሆነ ዕወቁ ። እስመ ኢመጻእኩ እጸውዕ ጻድቃነ ።

ጻድቃን ነን የምትሉ እናንተን ልጠራ አልመጣሁምና ።

አላ ኃጥአን ለንስሐ ።

ኃጥአን ነን የሚሉ እኒህን ወደ ንስሐ ልጠራ መጥቻለሁ እንጅ ፤ በዓለሙ አንድ ጻድቅ ኑሮ ያን ልጠራ አልመጣሁምና ሁሉ ኃጥእ ሁነዋልና ያን ልጠራ መጥቻለሁ እንጅ ።

፲፬ ወእምዝ መጽኡ ኀቤሁ አርዳኢሁ ለዮሐንስ ወይቤልዎ በእፎ ኢይጸውሙ አርዳኢከ ። ማር ፪ ፡ ፲፰ ። ሉቃ ፡ ፭ ፡ ፴፫ ።

፲፬ ለምንት ሲል ነው በእፎ ትጼዕል ሊቀ ካህናቲሁ ለእግዚአብሔር እንዲል ፤ ከዚህ በኋላ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት መጥተው ደቀ መዛሙርትህ ለምን አይጾሙም አሉት ።

ንሕነሰ ወፈሪሳውያን ንጸውም ብዙኃ ።

እኛ ፈሪሳውያን ግን ብዙ እንጾማለን ። ሐተታ ፡ ምን ጾም አላቸው ቢሉ እሑድና ማክሰኞ ሐሙስ ይጾማሉና ፤ አንድም ጾመ ረቡዕ ጾመ ሐሙስ ጾመ ሰቡዕ ጾመ አሱር የሚባል ጾም አለና ።

፲፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢይክሉ ደቂቀ ለመርዓዊ ጸዊመ ወላህዎ እምጣነ ሀሎ መርዓዊ ምስሌሆሙ ።

፲፭ የመርዓዊ ሚዜዎች መርዓዊ ከሳቸው ጋራ ሳለ መጾም ማልቀስ አይቻላቸውም ።

ወባሕቱ ይመጽእ መዋዕል አመ ይነሥእዎ ለመርዓዊ እምኔሆሙ ውእተ አሚረ ይጸውሙ ነገር ግን መርዓዊ ከሳቸው የሚለይበት ጊዜ ይደርሳል ያን ጊዜ ይጾማሉ አለ ፤ ዐሥርቱ ቢወጣ ፤ አንድም የኔ ደቀ መዛሙርት ከኔ ጋራ ሳሉ መጾም ማልቀስ አይቻላቸውም እኔ ከሳቸው የምለይበት ጊዜ ይደርሳል ያንጊዜ ይጾማሉ ፤ ይነሥእዎ ፀሞት ቢሉ

ሁለት ቀን ያከፍላሉና በዕርገት ቢሉ ፺ ቀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ይጾማሉና ።

፲፮ ወአልቦ ዘይጠቅብ ግምደ ደርግሀ ውስተ ስጠተ ልብስ ብሉይ ።

፲፮ አዲስ ቍራጭ ባረጀ ልብስ ላይ የሚጥፍ የለም ።
እስመ ይትመላዕ ሕያዎ ለልብስ ።
ደኅነኛውን ተሟልቶት ይሄዳልና ።
ወያዓብዮ ለስጠቱ ።
ቀዳዳውንም ያሰፋዋልና ፤ አንድም ሐዋርያትን በመንፈስ ቅዱስ ባልታደሰ ሰውነታቸው ጾምን ጹሙ የሚላቸው የለም ጾሙም ይቀራል ሰውነታቸውም ይጎዳልና ።

፲፯ ወአልቦ ዘይወዲ ወይነ ሐዲሰ ውስተ ዝቅ ብሉይ ።

፲፯ ባረጀ ራዋት ጉሽ ጠጅ የሚሾም የለም፤
ወእመ አኮስ ዝቁሂ ይነቅዕ ወወይኑሂ ይትከዓው ።
ቢሾሙ ግን ራዋቱም ይቀደዳል ወይኑም ይፈሳል።
ወባሕቱ ለወይንስ ሐዲስ ውስተ ዝቅ ሐዲስ ይወድይዎ ፤
ጉሹን ጠጅ ግን ባዲስ ራዋት ይሾሙታል ፣ ወይትዓቀቡ ፪ሆሙ በበይናቲሆሙ ።
እርስ በርሳቸው ባንድነት ይጠባበቃሉ ፣ አዲሱ ራዋት የጠጁን ፍላሎት ይችለዋል የጠጁም ፍላሎት አዲሱን ራዋት ያለፋዋልና ፣ አንድም ሐዋርያትን በልጅነት ባልታደሰ ሰውነታቸው ሕግ ጠብቁ የሚላቸው የለም ፤ ወእመ አኮስ ፤ ጠብቁ ቢሏቸውም ሕጉም ይፈርሳል ሰውነታቸውም ይጎዳልና ፣ ወባሕቱ ፣ በልጅነት በታደሰ ሰውነታቸው ግን ወንጌልን ጠብቁ ይሏቸዋል ፣ ወይትዓቀቡ ፣ እርስበርሳቸው ይጠባበቃሉ እሳቸውም ሕጉን ይጠብቁታል ሕጉም እሳቸውን ይጠብቃቸዋል ። አኮ ንሕነ ዘነዓቅቦሙ ለሕገጋት አላ እሙንቱ ሕገጋት የዓቅቡነ ለዓቂብ ወለተጸውኖ እንዲል ።

በእንተ ወለተ ኢያኢሮስ፣

ወበእንተ ደም ዘይውኅዛ ።

፲፰ ወእንዘ ዘንተ ይነግሮሙ ናሁ መጽአ አሐዱ መኰንን ወሰገደ ሎቱ ። ማር ፭፥፳፪።ሉቃ፥ ፰፥ ፵፩።

፲፰ ይህን ሲነግራቸው ኢያኢሮስ መጥቶ ሰገደለት ። እንዘ ይብል ወለትየ ይእዜ ሞተት ። ልጄ ዛሬ ሞተች አለው ።
ወባሕቱ አንብር እዴከ ላዕሌሃ ወተሐዩ ።
ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት ትነሳለች አለው።
፲፱ ወተንሢኦ ሖረ ።
፲፱ ትንሥቶ ሄደ ።
ወተለውዎ ብዙኃን ሰብእ ።
ብዙ ሰዎች ተከተሉት ።
ወአርዳኢሁኒ ምስሌሁ ፤
ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ሄደ ፣

፳ ወናሁ መጽአት ብእሲት እንተ ደም ይውኅዛ እም፲ ወ፪ቱ ክረምት ወቀርበት እንተ ድኅሬሁ ። ማር ፭፥ ፳፭ ። ሉቃ ፰ ፣ ፵፫ ።

፳ ካሥራሁለት ዓመት ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት መጣች ። ዘ፲ቱ ወ፪ቱ ዓመት ይላል ደም መፍሰስ ከጀመራት ፲፪ ዓመት የሆናት ሴት ከወደኋላው መጣች ።

፳፩ ወገሠሠት ጽንፈ ልብሱ እንዘ ትብል በልባ እምከመ ገሠሥኩ ጽንፈ ልብሱ አሐዩ ።

፳፩ የልብሱን ዘርፍ የዳሰስሁ እንደሆነ እድናለሁ ብላ የልብሱን ዘርፍ ዳሰሰች ።

፳፪ ወተመይጠ እግዚእ ኢየሱስ ርእያ ።

፳፪ ጌታም ተመልሶ አያት ።
ወይቤላ ተአመኒ ወለትየ ሃይማኖትኪ አሕየወተኪ ልጄ ሃይማኖትሽ አዳነችሽ በሃይማኖትሽ ጽኚ አላት እንዲያው አይደለም ወደ ኋላ ተመልሶ ደቀ መዛሙርቱን መኑ ገሠሠኒ ጽንፈ ልብስየ አላቸው ከዚህ በኋላ ናሁ ብዙኀ ሰብእ ይጸዓቅ ወይጣወቅ አንተስ ትብል መኑ ገሠሠኒ ጽንፈ ልብስየ አሉት ፤ ታምራት ያደርጋል ነገር ግን ይሰረቀዋል እንጅ እንዳይሉ አእምር ከመ ወፅአ ኃይል እምኔየ ብሏቸዋል ነገሩ ካልቀረስ ብላ ወደፊቱ አልፋ ሰገደችለት ። ከዚህ በኋላ ተእመኒ ወለትየ ብሏታል እንተ ደም ይውኅዛ የቤተ አይሁድ ልብስ የሐዋርያት አልባሲሁስ ለክርስቶስ መሃይምናን እሙንቱ እንዲል ፤ ጽንፈ ልብስ ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ መምህራን ፣ እንተ ደም ይውኅዛ የልብሱን ዘርፍ ይዛ እንደተፈወሰች ቤተ አይሁድም ከሐዋርያት ቀጥለው ከተነሡ መምህራን ተምረው ስብ ማጤሳቸውን ደም ማፍሰሳቸውን መተዋቸውን መናገር ነው ወሐይወት ሶቤሃ ይእቲ ብእሲት ።
ፈጥና ያን ጊዜ ዳነች ።

፳፫ ወመጺኦ እግዚእ ኢየሱስ ቤቶ ለውእቱ መኰንን ረከበ ሰብአ ብዙኃነ መብክያነ እንዘ ይትሀወኩ ።

፳፫ ጌታችን ከኢያኢሮስ ቤት በደረሰ ጊዜ ብዙ ሰዎች ሲያለቅሱ ሲወጡ ሲገቡ አገኘ ፤ ሹም ቢሞት ፺ የሹም ልጅ ቢሞት መቶ ታምሳ እንዲሉ ።
፳፬ ወይቤሎሙ ተገኃሡ ።
፳፬ ተመለሱ አላቸው ።
እስመ ኢሞተት ሕፃን ።
ብላቴናይቱ አልሞተችምና ።
አላ ትነውም ።

ተኝታለች እንጂ ፡ እንዲያሥነሣት ያውቃልና በነፍስ ሕያዊት ናትና ትቀድሰዋለችና ።
ወሰሐቅዎ ፤
በኢያኢሮስ ሳቁበት የሞተና ፤ ያልሞተ የማያውቅ ያሥነሣልኛል ብሎ ይዞ መጣ ብለው ፤ አንድም የጌታን ነገሩን እንደ ዋዛ አዩበት ያጠብን የገነዝን ። እኛ እያሰን አልሞተችም ይለናል ፡ ብለው ።

፳፭ ወእምዝ ወፅአ ሰብእ ቦአ ወአኃዛ እዴሃ ፤
፳፭ ሰዎቹ ከወጡ በኋላ ገብቶ እጇዋን ይዞ አሥነሣት ።
ወተንሥአት ሕፃን ።
ብላቴናይቱ ተነሣች ። ሐተታ እንተ ደም ይውኅዛ የታመመችበት ይህች ብላቴና የተወለደችበት እንተ ደም ይውኅዛ የተፈወሰችበት ይህች ብላቴና የተነሣችበት ቀኑ አንድ ነው ።

፳፮ ወወፅአ ስሙዓት ነገሩ ውስተ ኵሉ በሐውርት ።

፳፮ የተአምራቱ ዜና ስሙዓተ ነገራ ይላል ቀድሞ መሞቷ ኋላ መነሣቷ በራቱ ማዕዘን ተነገረ ፤

በእንተ ፪ቱ ዕውራን

፳፯ ወኃሊፎ እግዚእ ኢየሱስ እምህየ ተለውዎ ፪ቱ ዕውራን
፳፯ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚያ አልፎ ሲሄድ ሁለት ዕውራን ተከተሉት ።
እንዘ ይጸርሑ ወይብሉ ተሣሃለነ ወልደ ዳዊት ።
ወልደ ዳዊት እዘንልን ይቅር በለን እያሉ ።
፳፰ ወበዊአ ቤቶ መጽኡ ኀቤሁ እሙንቱ ዕውራን ።

፳፰ ለዕውራን ርቆ መሄድ አይሆንላቸውምና ከቤት ገብቶ ቆይቷቸዋል ከቤት በገባ ጊዜ ዕውራን ወደሱ መጡ ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ተአምኑሁ ከመ እክል ዘንተ ገቢረ ።
ጌታም ዕውር ማዳን እንዲቻለኝ ታምናላችሁን አላቸው ።
ወይቤልዎ እወ እግዚኦ ።
አቤቱ እዎን እናምናለን አሉት ፡ ሐተታ እወ እንዲሉት ያውቅ የለም ቢሉ ዐላዋቂ ሥጋን እንደተዋሐደ ለማጠየቅ ፡ አኮ ኢያእምሮ ኅቡአተ ፡ አላ ከመ የሀብ መካነ ለጥንተ ትሰብእቱ ዘኢየአምር ኅቡአተ ፡ እንዲል ፡ አንድም ፡ ዐወቅሁት ብሎ ሥራውን አይተውምና ፤ በዚያው ሥራውን ለመሥራት አንድም ፡ ሃይማኖታቸውን ለማስገለጽ ።
፳፱ ወገሠሦሙ አዕይንቲሆሙ ።
፳፱ ዓይናቸውን ዳሠሣቸው ።
ወይቤሎሙ በከመ ሃይማኖትክሙ ይኩንክሙ ።
እንደ ሃይማኖታችሁ ይደረግላችሁ አላቸው ።

፴ ወሶቤሃ ተከሥተ አዕይንቲሆሙ
፴ ያን ጊዜ ዓይናቸው ዳነ ።
ወገሠጾሙ እንዘ ይብል ዑቁ ኢትንግሩ ለመኑሂ ።
ለማንም ለማን እንዳትነግሩ ዕወቁ ብሎ አስተማራቸው ውዳሴ ከንቱ አይሻምና የሚያምኑበት ጊዜ አልደረሰምና ፡ አንድም እስከ ትንሣኤ ፡

፴፩ ወወፂኦሙ ነገሩ ለኵሉ ብሔር

፴፩ ወጥተው ለሰው ሁሉ ተናገሩ አትንገር ያሉት ሰው መንገር ልማድ ነውና ፡ አንድም ጊዜው ቢደርስ ።
በእንተ ጽሙም ዘቦቱ ጋኔን ፤

፴፪ ወእምዝ አምጽኡ ኀቤሁ ዘጋኔን ጽሙመ ወበሀመ ፡ ማቴዎስ ፲፪ ፡ ፳፪ ፡ ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ።

፴፪ ከዚህ በኋላ ጋኔን ድዳ ደንቆሮ ያደረገውን ሰው ይዘው መጡ ። ድዳ ደንቆሮ ጋኔን ሲያድርበት ሰውም ድዳ ደንቆሮ ይሆናልና ፡ አንድም ጽሙም ወበሐም ይላል ድዳ ደንቆሮ ጋኔን ያደረበትን ሰው ይዘው መጡ ፡ ቀድስ ቢሉት አልቀድስም ብሏልና ፡ ድዳ አሰው ። ትእዛዘ እግዚአብሔርን ስማ ቢሉት አልሰማም ብሏልና ደንቆሮ አሰው ።
፴፫ ወወፂአ ጋኔኑ ነበበ ውእቱ በሐም ወሰምዓ ውእቱ ጽሙም

፴፫ ጋኔኑ በተለየው ጊዜ ድዳ የነበረው ተናገረ ደንቆሮ የነበረው ሰማ ።

፴፬ ወፈሪሳውያንሰ ይቤሉ በመልአኮሙ ለአጋንንት ያወፅኦሙ ለአጋንንት ።

፴፬ ፈሪሳውያን ግን ታምራት ያደርጋል ሰው ይሳባል ኦሪት ትጠፋለች ወንጌል ትሰፋለች ብለው የንጉሥን ጭፍራ በንጉሥ ቀላጤ እንዲያስወጡት ካለቃቸው ከብዔል ዜቡል ተጨዋውቶ ያስወጣቸዋል እንጂ እሰዚያ ግን አያስወጣቸውም አሉ ። አሁን ለነዚህ ዛሬ አይመስላቸውም በሚመጣው ጉባኤ ይመልስላቸዋል ።

በከመ አንሶሰወ ኢየሱስ ውስተ ገሊላ

፴፭ ወአንሶሰወ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ኵሉ አህጉር ወበሐውርት እንዘ ይሜህር በምኵራባቲሆሙ ። ማር ፮ ፡ ፮ ።

፴፭ ጌታ በምኵራባቸው እየገባ ሲያስተምር ኖረ ወይሰብክ ወንጌለ መንግሥት ጌትነቱን የምትናገር ወንጌልን ሲያስተምር ኖረ ። ሐተታ እንዳለፈው ምዕ ፡ ፬ ፡ ፳፫ ።

ወይፌውስ ኵሎ ድዉያነ ወኵሎ ሕማመ ዘውስተ ሕዝብ ለዚያው ምልክት በሕዝቡ ዘንድ ያሉ ድውያንን ሁሉ ይፈውስ ነበረ ።

፴፮ ወርእዮ ብዙኃነ ሰብአ እምህርዎ ፡ ወተማሃሎሙ ።

፴፮ ብዙ ሰዎችን ባየ ጊዜ አሳዘኑት ፡ አዘነላቸው
እስመ ስሩሃን እሙንቱ ።
በጾማ አራት በጾማ ኃጢአት ደክመዋልና ።
ወግዱፋን ከመ አባግዕ ዘአልቦ ኖላዌ ።
ጠባቂ እንደሌላቸው አባግዕ ሁነዋልና ።

፴፯ ወእምዝ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ፡ ሉቃስ ፲ ፡ ፪ ።

፴፯ ከዚህ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው ።
ማዕረሩሰ ብዙኅ
መከሩ ብዙ ነው
ወገባሩ ኅዳጥ ።
ሠራተኛው ግን ጥቂት ነው ።

፴፰ ሰአልዎ ለበዓለ ማዕረር ።
፴፰ የመከሩን ባለቤት ለምኑት ።
ከመ ይወስክ ገባሬ ለማዕረሩ ።

ለመከሩ አጫጅ ሠራተኛ ይጨምር ዘንድ ፤ አንድም ማዕረሩስ ብዙኅ ሰማዕያኑ ብዙ ናቸው ። ወገባሩ ኅዳጥ መምሩ አንድ የሐንስ ነው ወኅዳጥ ዓቀ እንዲል ሰአልዎ የመምርነት ባለቤት እኔን ለምኑኝ ፡ ከመ ይፌስስ እናንተን መምሀራን አድርጌ እሾማችሁ ዘንድ ወደፊት በሚያመጣው ሹመት አትለምኑ ይል የለም ከዚህ ምነው እንዲህ አለ ቢሉ ፡ ያ ሥጋዊ ነው ይህ ግን መንፈሳዊ ነውና የሚጠቀሙበትም ነውና ፡ አንድም አስፈቅዶ ለመሾም መከራ በመጣባቸው ጊዜ ተሾሙ ተሾሙ ያለን ለዚህ ነው እንዲሉ ፡ ምነዋ መከራ ብንቀበል ወደን እንጂ ተሹመነዋል እንዲሉ ፡ አንድም ማዕረሩ ብዙኅ ፡ መጻሕፍተ ነቢያት ንባባቸው ብዙ ነው ወገባሩ ሕዳጥ ፡ ትርጓሜያቸው ጥቂት ነው ። ድኅነት አያሰጡም ። ሰአልዎ ፡ የብሉይ የሐዲስ ባለቤት እኔን ለምኑኝ ከመ ይወስክ ገባሬ ፡ መተርጕማን አድርጌ እሾማችሁ ዘንድ ድኅነት እንድታሰጡ አደርጋችሁ ዘንድ

በከመ ተፈነወ ሐዋርያት ።

ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወጸውዖሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ አርዳኢሁ ። ማር ፫ ፡ ፲፫ ። ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፲፫ ፡ ፱ ፡ ፩ ።

፩ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ጠራቸው ማለት ሾማቸው ወወሀቦሙ ሥልጣነ ዲበ መናፍስት ርኩሳን ከመ ያውፅእዎሙ ወይፈውሱ ኵሎ ደዌያነ ወሕሙማነ ።

አጋንንት ያወጡ ድውያን ይፈውሱ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው ማለት ለሹመታቸው ምልክት ድውያን ይፈውሱ ሙታን እንሥኡ እለ ለምጽ እንጽሑ ብሎ ዝርዝሩ ታምራትን ሰጣቸው ፡ ንጉሥ ደጃዝማች በሾመ ጊዜ ለሹመቱ ምልክት ስንደቅ አላማ ማሠሪያ ነጋሪት ሰጥቶ እንዲሰደው ዐሥራ ሁለት መሆናቸው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ፡ ትንቢት ፡ ኤርምያስ ለሊሁ ኢየሱስ አምላክ ወልደ አምላክ ይመጽእ ውስተ ዓለም ወየኀሪ ፲ተ ወ፪ተ ሐዋርያተ ወይከይድ ውስተ ደብረ ዘይት ዘእነ ርኢኩ ሥግወ ብኋል ፤ ኤልሳዕም በራእዩ ወናሁ ይወርድ እግዚእን እምሰማይ ዲበ ምድር ወየኀሪ ፲ተ ወ፪ተ ዕፀወ ባሉጥ ብኋል ፤ ምሳሌም ያዕቆብ ከአዋልደ ከነዓን አልተጋባም ሶርያ ወርዶ ፲፪ ሕፃናት ወልዷል ጌታም ባሕርየ መለኮትን ባሕርይ አላደረገም የአዳምን ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ ፀሥራሁለቱን ሐዋርያት ሹሞ መሰደዱን መናገር ነው ። ኢንሥእ ለዘንሥእ እመላእክት ዘእንበለ ዘርዐ አብርሃም እንዲል ፡ ለነዚያ ሦስቱም ምውታን ዐሥራው አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ አሏቸው ለነሆም ፫ ሐያዋን ዐሥራው ሥላሴ አሏቸውና በዐሥራሁለቱ ምዕዛረ ፀሐይ በእሥራሁለቱ አልህምተ ብርት በዐሥራሁለቱ መገብተ ሰሎሞን በዐሥራ ሁለቱ የቤት አለቆች በፀሥራ ሁለቱ ጉበኞች ምሳሌ ፡ ወግእዙ እሥራኤል ወበጽሖ ኀበ ፲ቱ ወ፪ቱ አንቅዕት ወ፸ ተመርት ይላል ዐሥራ ሁለቱ አንቅዕት የሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ፸ ተመርት የ፸ አርድእት ምሳሌ ። አንድም በልብሰ አሮን ባሉ በዐሥራ ሁለት አይናቍ ምሳሌ ። በደብረ ሲና ከዙፋኑ እግር በተገኙ በ፲፪ቱ አዕናቍ ፡ ኤልያስም ፲፪ ቻል ውኃ አምጡ ብሎ ደግሙ ሠልሱ ብሏቸዋል በዚያ ምሳሌ ኢያሱ ዮርዳኖስን ሲሻገር ዐሥራሁለት ድንጊያ ከአፍአ አግብቶ ቢውስጥ ተክሏል ዐሥራ ሁለት ድንጊያ ከባሕሩ አውጥቶ አሸክሞ ወስዶ ፲፪ቱን በጌባል ፲፪ቱን በገሪዛን አስተክሏቸዋል ሰዎቹ የሐዋርያት ድንጊያው የመከራቸው ምሳሌ ትንቢቱን ዐውቆ አናግሯል ምሳሌውንም እንጂ ባወቀ አስመስሏል ምሥጢሩ እንደምን ነው ቢሉ ለአራት ባሕርያት ሦስት ሦስት ግብር አላቸው ። ዐሥራ ሁለት ይሆናል ካራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሰውን እጠብቅባቸዋለሁ ሲል ።

፪ ወዝንቱ አስማቲሆሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ሐዋርያት ።

፪ ያሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስማቸው ይህ ነው ። ሐዋርያት ማለት ደጃዝማች ቀላጤ ምጥው ፍንው ሃያጅ ማለት ነው ። ደጃዝማች በተሾመበት አገር ገብቶ የተቀበለውን ሹመት ሽልማት ሰጥቶ ያከብረዋል ። ካህን ቢሆን ዐሥራቱን በኵራቱን ሰጥቶ ያከብረዋል ። ይህን የማይሻ መነኵሴ ቢሆን ከእ

ግሩ ቆድቶ አቡነ ዘበሰማያት ይቀበላል ለመነኩሲው ክብሩ ነው ያልተቀበለውን ዓይን በፍላት እጅ እግር በስለት ይቆጣል ። ሐዋርያት ትምህርታቸውን የተቀበሏቸውን በልጅነት ያከብራሉ ሀብት ሥርየት ይሰጣሉ ያልተቀበሏቸውን በሌጌዎን ይነጸሉ በኑፋቄ ይሰቅላሉና ፤ ቀላጤም በደለኛ ወታደር ካልገዛው አገር ገብቶ ያልፈላ ያስጠምቃል ያልቦካ ያስጋግራል ። የተበደለ ድኃ ከንጉሥ ሄዶ ይሞግታል ባዳራሽ ተገኝቶ ቀላጤ ሰጥቶ ይሰደዋል ፤ ያ ቀላጤ በብርሃን የገባውን በጨለማ በፀሐይ የገባውን በዝናም አስወጥቶ የተሰበረ ዕንጨቱን የተቀዳ ውኃውን ያስመልሰለታል ። በደለኛ ወታደር ካልገዛው አገር ገብቶ ያልፈላ እንዲያስጠምቅ ያልቦካ እንዲያስጋግር ፤ ዲያብሎስ ያልፈጠረውን ፍጥረት ያልገዛውን ሰውነት ፭ ሽህ ካ፭፻ ዘመን ኃጢአት ሲያሰራ ጣዖት ሲያሰልክ መኖሩን መናገር ነው የተበደለ ድኃ ከንጉሥ ሄዶ እንደመጮህ ነቢያት እንሥእ ኃይለከ ፈኑ እዴከ ማለታቸውን መናገር ነው ንጉሥ ባዳራሽ ተገኝቶ ቀላጤ ሰጥቶ እንደ መስደድ ቃለ እግዚአብሔር ሰው ሁኖ በሥራ ሁሉቱን ሐዋርያት ሹሞ መሰደዱን መናገር ነው ። ቀላጤ በብርሃን የገባውን በጨለማ በፀሐይ የገባውን በዝናም እንዲያስወጣ ሐዋርያትም በደዌ የገባውን በታምራት በክህደት የገባውን በትምህርት ማስወጣታቸውን መናገር ነው። የተሰበረ ዕንጨቱን እንዲያስመልሰለት በአዳም የሄደውን ልጅነት አስመልሰዋልና ፤ ፍንው ፤ ወናሁ አነ እፌንወክሙ ከመ አባግዕ ማእከለ ተኩላት ብሎ እንዲያመጣው ምጥው ። ከፍንው ይገባል ፤ ሃያጅም እለ ይህ ሁሉ ካልሄዱ አይገኝምና ።

ቀዳሚ ስምዖን ዘተሰምየ ጴጥሮስ ።

አንዱ መጀመሪያው ጴጥሮስ የተባለ ስምዖን ነው ። ሐተታ ፤ ጴጥሮስ ማለት መርግ ማለት ነው መርግ ከወደላይ ቢመጣ ያስፈራል ። እሱም ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ እያለ ሲያስተምር ያስፈራልና አንድም ሻር ደንጊያ ማለት ነው ይህ ሥጋን ካጥንት ይለያል ። እሱም ምእመናንን ከመናፍቃን ይለያልና ፤ አንድም ደንጊያ ማለት ነው ይህን የቀን ሐሩር የሌሊት ቁር አይለውጠውም ። እሱም በመከራ አይለወጥምና ፤ አንድም ከዋው ደንጊያ ማለት ነው ያ እየፈጋ ይሄዳል ። እሱም ካ፲፩ዱ ሰብከት ሁሉ እየገባ ያስተምራልና ፤ ወእንድርያስ እኁሁ ።

ወንድሙ እንድርያስ ነው ። ሐተታ ፤ እንድርያስ ማለት ተባእ ለመስቀል በዞረ ሐዋርያት ማለት ነው ።

፫ ወያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ

፫ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብ ነው ሐተታ ፤ ያዕቆብ ማለት አዕቃጺ እኃዚ ማለት ነው ። የቀደመው ያዕቆብ ስኩና ኤሳውን ይዞ እንደተወለደ ፤ እሱም ስኩና ወንጌልን ይዞ ሲያስተምር ይሞታልና ስኩና ኤሳውን እንዳስናከለ እሱም የመናፍቃንን ትምህርት ያሰናክላልና ።

ወዮሐንስ እኁሁ ።

ወንድሙ ዮሐንስ ነው ። ዮሐንስ ማለት ፍሥሐ ወኀሤት ማለት ነው ። ወብዙኃን ይትፌሥሑ በልደቱ እንዳለ ፤ ፊልጶስ ።

ፊልጶስ ነው ፤ ፊልጶስ ማለት ረያጼ አፍራስ ማለት ነው አኃዜ ኩናትም ማለት ነው መፍቀሬ አኃው ማለት ነው ፊልሳዳፎስ እንዳለ ።

ወበርተሎሜዎስ

በርተሎሜዎስ ነው በእብራይስጥ በር ልጅ ማለት ነው ። ተክል የማጠጣት ግብር ያለው ልጅ ማለት ነው ወልደ ኃይል ወልደ የማን እንዳለ ፤ አንድም ወይን ተክሎ ዕለቱን አድርሷልና ፤

ቶማስ ።

ቶማስ ነው፤ ቶማስ ማለት ፀሐይ ማለት ነው ። ፪ቱ እስማቲሁ ለፀሐይ አሐዱ ቶማስስ ወ፩ዱ ኦርያሬስ እንዳለ ።

ወማቴዎስ መጸብሐዊ ።

አንዱ ማቴዎስ ነው ። ማቴዎስ ማለት ኅሩይ ማለት ነው ከዚህ አውጥቶ ለዚህ ማዕርግ አበቃው ሰማለት ስሙን ከነግብሩ ጠራው ።

ወያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ።

የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ነው ሐተታ ፤ እንዳሰፈው ወልብድዮስ ዘተሰምየ ታዴዎስ፤ ታዴዎስ የተባለ ልብድዮስ ነው ልብድዮስ ማለት ልብደ ሠረ ዓማ ወጋሪ ማለት ነው ። ልበ ድዮስ ይላል ካህነ አምላክ ማለት ነው ። ወእምጽአ ማሬ ዘድዮስ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ሕዝበ ድዮስጳራ እንዳለ ፤ አንድም ዘርዕ ወማዕረር ማለት ነው አሪትን እንደ ዘር ወንጌልን እንደ መከር አድርጎ አስተምሯልና አንድም ሥንዴ ዘርቶ ዕለቱን ለመሥዋዕት አድርሷልና

፬ ወስምዖን ቀነናዊ ።

፬ ባልተነበበ ስሙ ይተረጉማሉ ስምዖን ያለው ናትናኤል ነው ናትናኤል ማለት ውሁብ ሀብተ እግዚአብሔር ማለት ነው ቀነናዊ የቃና ሰው ቀሬናዊ የቀራንዮ ሰው ቀናኢ ለሕገ አምላኩ ።

ወይሁዳ አስቆሮታዊ ዘውእቱ አግብኦ ።

የአስቆሮት ሰው የሚሆን ያስያዘው ይሁዳ ነው ። ይህ ሰው ስሙ ከግብሩ ያልተባበረ ነው ይሁዳ ማለት ተአማኒ በእግዚአብሔር ማለት ነበር እሱ ግን አላደረገውም ለዚህ ማዕርግ ቢያበቃው ከሞቱ ገባበት ለማለት ጸፈው እንዳወጣው ለማጠየቅ በመጨረሻ አመጣው ።

፭ እሉንተ ዐሠርተ ወ፪ተ ሐዋርያተ ፈነዎሙ እግዚእ ኢየሱስ ።

[illegible] እሉንተ ካለ ፈነወ ፈነዎሙ ካለ ለእሉንቱ [illegible] ዐሥሩ ነበር ፤ ጌታ እኒዚን ፲፪ቱን ሐዋርያት ላክ [illegible] መርጦ ሾሞ ሐተታ ካ፰ ወገን መርጧቸዋል፤ ከእናምያን ከፈላጭያን ከመጸብሐን ከመሠግራን ከመስተገብራን ፥ ቤትን ባምስት ወገን ያጸኑታል [illegible] በገለባ በጭቃ በደንጊያ በእንጨት ካራት ባሕርያት ካ፰ኛ ባሕርየ ነፍስ የተፈጠረ ሰውን [illegible] አጠብቀባችኋለሁ ሲል ፤ ከነዚህም [illegible] [illegible] ያሰወጠውም አለ ። በአ[illegible] ያላዳለፈውም ግብር እንዳለ ለማ[illegible] ፤ [illegible] ገውጣትም የገዢና የተገዢ ምልክት [illegible] [illegible] ሰው ስሙን ለውጦ እንዲያወጣ [illegible] እንዘ ይብል ፍኖተ አሕዛብ ኢትሑሩ ፤ [illegible] መንገድ አትሂዱ ማለት የአሕዛብን ሥራ አትሥሩ ። ወውስተ ሀገረ ሳምር ኢትባኡ ፤ ወደ ሳምራውያንም አገር አትግቡ ብሎ አዘዛቸው ።

፮ ወሑሩ ባሕቱ ኀበ አባግዕ ዘተኀጕላ እምቤተ እስራኤል ።

፮ [illegible]ራኤል ወደ ጠፉ በጎች ሂዱ ማለት መምህር አብነት ትምህርት አጥተው ወደ ተጎዱ ወደ እስራኤል ሂዱ እንጂ ትንቢት የተነገረ ሱባዔ የተቈጠረ ለነዚህ ነውና አንድም ። ትንቢት የተነገረልን ሱባዔ የተቈጠረልን እኛ ባለን ትምህርቱን [illegible] [illegible] [illegible] ገባንበት ባሉ ነበርና ፤ አንድም [illegible] [illegible] ፥ አንድም በመንፈስ ትዕቢት [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] በኋላ ነበርና እንዳይሉ ፤

፯ ወሐዊረክሙ ስብኩ እንዘ ትብሉ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ፤

፯ ሂዳችሁ ድኂቱ በልጅነት ልጅነት በሃይማኖት የምትሰጥበት ጊዜ ደርሷል እያላችሁ አስተምሩ

፰ ድውያነ ፈውሱ ።

፰ ድውያንን ፈውሱ ። ሙታነ አንሥኡ ፤
ሙት አንሡ ።
እለ ለምጽ አንጽሑ ፤
ለምጽ አድኑ ።
አጋንንተ አውጽኡ ፤
አጋንንትን አውጡ ።
በጸጋ ዘነሣእክሙ በጸጋ ሀቡ
በለጋስነት የተማራችሁትን በለጋስነት አስተምሩ
በከንቱ ዘነሣዕክሙ በከንቱ ሀቡ
ዋጋ ሳትሰጡ የተማራችሁትን ዋጋ ሳትቀበሉ አስተምሩ አንድም በጸጋ ዘነሣእክሙ ፥ በታምራት የተማራችሁትን በታምራት አስተምሩ ፥ በከንቱ ዘነሣእክሙ ፥ ሳትጽፉ የተማራችሁትን ሳይጽፉ አስተምሩ

፱ ኢታጥርዩ ለክሙ ወርቀ ወኢብሩረ ፥ ማር ፮ ፥ ፰ ፥ ሉቃ ፥ ፱ ፥ ፫ ፥ ፲ ፥ ፬

፱ ወርቅ ብር አትያዙ ።
ወኢጸሪቀ ውስተ ቅናውቲ ክሙ ።
በዝናራችሁ ቍናማቺክሙ ይላል ፥ በተረንተራችሁ ሻሚ መሐልቅ አትያዙ ።

፲ ወኢጽፍነተ ለፍኖት ።

፲ የስንቅ አቅማዳም አትያዙ ።
ወኢክልኤ ክዳናተ ።
ሁለት ልብስም አትያዙ ፥ ይህን የሚሹ ሥጋውያን ናቸው እሳቸው ግን መንፈሳውያን ናቸውና ይህን አይሹም ፤ አንድም ሁለትም ልብስ ባይኖረን አንዱን ለብሰን አንዱን ሸጠን ባንመገብ እንደምን በሆን ነበር ብሎ ያዳክማልና እንዳያዳክማቸው ነው
ወኢ.ዓሣዕነ ።
ጫማ አታድርጉ ይህ ለሥጋውያን ነው ፤ እሳቸው ግን መንፈሳውያን ናቸውና ይህን አይሹትም ፤ አንድም ጫማ ባይኖረን እሾሁን ዕንቅፋቱን ዋዕዩን እንደምን ባለፍነው ነበር ብሎ ያዳክማልና እንዳያዳክማቸው ነው ። አንድም ጌጸኛውን ሲል ነው።
ወኢበትረ ።
በትርም አትያዙ ። ይህ ለሥጋውያን ነው ፤ እሳቸው ግን መንፈሳውያን ናቸውና ይህን አይሹትም ፥ አንድም በትር ባንይዝ ውሻው ጅባቡ እንደምን ባደረገን ነበር ብሎ ሃይማኖት ያዳክማልና እንዳያዳክም ነው አንድም ጌጸኛውን ሲል ነው እስመ ይደልዎ እስቡ ለዘይትቀነይ ።
ለሚሠራ ዋጋ ይገባዋልና ለሚያስተምር መምህር የዕለት ራት አንድ እንጀራ ጽዋ ውኃ ይገባዋልና ። ኢታጥርዩ ። አንድም በናስተምር ውለን ምን እን መገባለን ትሉኝ እንደሆነ ለሚያስተምር ለመምህር እንጂ የለት ራት አንድ እንጀራ ጽዋ ውኃ ይገባዋል እነዚያው ይመግቧችሁ ።

፲፩ ወውስተ ሀገር እንተ ቦእክሙ ወኾመኒ አብያት ተስእሉ ወበሉ ለመኑ ይደልዎ ሰላም በውስቴታ ።

፲፩ ከገባችሁበት አገር ከገባችሁበት ቤት ደግ ሰው የበቃ ማን አለ ብላችሁ ጠይቁ ።
ወሀየ ኅድሩ እስከ አመ ትወጽኡ ፤
ለማስተማር ወጥታችሁ እስክትሄዱ ድረስ ከዚያ ኑሩ ። ሐተታ፥ምእመናን ለመማር በመጡ ጊዜ እንዳያጧቸው ነው ። አንድም ካንዱ ወዳንዱ ሲሉ ያይዋቸው እንደሆነ እኒህማ ምግብ ለማሻሻል መጥተዋል እንጂ መቼ ለማስተማር መጥተዋል እንዳይሏቸው ።

፲፪ ወበዊዓክሙ ውስተ ቤት ተአምኅዎሙ ።

፲፪ ከቤት በገባችሁም ጊዜ እጅ ንሷቸው ማለት አክብሯቸው እንጂ አክብሩን አትበሉ ።
ወለእመ ይደልዎ ለውእቱ ቤት ይኅድር ሰላምክሙ

ላዕሌሁ የበቃ ደግ ሰው የተገኘ እንደሆነ ሰላማችሁ እኔ አደርበታለሁ ።

፲፫ ወእመሰ ኢይደልዎ ይግባእ ሰላምክሙ ላዕሌክሙ ።

፲፫ የበቃ ደግ ሰው ያልተገኘ እንደሆነ ግን ሰላማችሁ በናንተ ይደር ማለት ሰላማችሁ እኔ በናንተ እንዳደርኩ አቀራለሁ ።

፲፬ ወለዘሰ ኢተወክፈክሙ ወኢሰምዓ ነገረክሙ ወፂአክሙ አፍአ እምውእቱ ቤት ወእም ውእቱ ሀገር ንግፉ ጸበለ እገሪክሙ ።

፲፬ እናንተን አልቀበልም ትምህርታችሁንም አልሰማም ያለ ሰው ካለበት ቤት ካለበት አገር ወጥታችሁ የግራችሁን ትቢያ አራግፉ ። ሐተታ ፥ ስንኳን ገንዘባችሁ ትቢያችሁ አልተከተለንም ለማለት ። እኛ ያክመንላችሁ በእምቢታችሁ ቢቀርባችሁ ፍዳችሁ በራሳችሁ ነው ለማለት ፥ አንድም ይህ ትቢያ ከኛ እንደተለየ እናንተም ከኛ ልዩ ናችሁ ለማለት ፥ አንድም ትቢያ እንደ ረገፈ እናንተም በሥጋችሁ በመቅሠፍት በነፍሳችሁ በገሃነም ትጠፋላችሁ ለማለት ፥ አንድም በቄሣር ልማድ ፥ የተበደለ ሰው ቢኖር ስንጨት ተክሎ ማር ጳጥሮ መጥቶ ይነገረኝ ብሎ ነበርና ።

፲፭ አማን እብለክሙ ከመ ይረክባ ሳሕተ ምድረ ሰዶም ወገሞራ እመ ዕለተ ደይን ፈድፋደ እምይእቲ ሀገር ።

፲፭ እናንተን አልቀበልም ትምህርታችሁን አልሰማም ያለ ሰው ኹሉ ካለበት አገር ይልቅ ሰዶም ገሞራ በፍርድ ቀን ዕረፍትን ያገኛሉ ብየ እንዲያገኙ በእውነት እነግራችኋለሁ ። በሀገሩ ሰዎቹን መናገር ነው ፍዳ ይቀልላቸዋል ማለት ነው ።

፲፮ ወናሁ አነ እፌንወክሙ ከመ አባግዐ ማእከለ ተኩላት ። ሉቃ ፲፥ ፫

፲፮ ተኩላ አለና ብለው አባግዕን ከቤት እንዳያወጧቸው ተኩላ ወዳለበት እንዲያሰማሯቸው ፥ ወደ ነገሥተ አሕዛብ ወደ መኳንንተ አሕዛብ እሰዳችኋለሁና ። ኩኑ እንከ ጠቢባነ ከመ አርዌ ምድር ወየዋሃነ ከመ ርግብ እንደ እባብ ብልሀ ሁኑ እንደ ርግብም የዋሀ ሁኑ ። አንድም በሉቃስ እፌንወክሙ ማእከለ ተኰላት ይላል ። ወደ ነገሥተ አሕዛብ ወደ መኳንንተ አሕዛብ እሰዳችኋለሁና ኩኑ ጠቢባነ ። ሐተታ የእባብ ብልሐቱ ምንድነው ቢሉ ከመንገድ ዳር ሲተኛ ራሱን ቀብሮ ይተኛል እናንተም ራሳችሁን እኔን አትካዱኝ ሲል አንድም ውኃ ሲጠጣ መርዙን ከየብስ አኑሮ ነው ፥ ከውኃው የገባ እንደ ሆነ ተሰራጭቶ ያጠፋኛል ብሎ እናንተም ቂም በቀል ይዛችሁ አትጸልዩ ሲል ቂም በቀል ይዞ የጸለዩት ጸሎት አይረባም አይጠቅምምና ። እስመ ዘያነብር ቂመ ውስተ ልቡ ኢይወጽእት ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር እንዲል አንድም በኖኅ ጊዜ አፉን ከፍቶ ሳለ ርግብ ዋሻ መስኮቱ ገብታ እንቁላሏን ጣለች እሷን የበላኋት እንደሆነ ኖኅ አስወጥቶ ይጥለኛል ብሎ እስክትወጣ አፉን እንደከፈተ ቆይቷል ምክንያት አድርጎ እናንተን የሚያጠፉበትን ሥራ አትሥሩ ሲል ነው ። አንድም ዕፀ ዘዌ የሚባል አለ ፍሬውንይወደዋልጥላውሊያርፍበትያደክመዋልብልሀ ኅውና ቤት በምሥራቅ ማታ በምዕራብ ሁኖ ይመግበዋል ምክንያት አድርጎ እናንተን የሚያዳክምበትን ሥራ አትሥሩ ሲል ፥ አንድም ጥግ ላይዝ አይጣላም ምክንያት አድርጎ እናንተን የሚጣላበትን ሥራ አትሥሩ ሲል ራቁቱን የሆነ አይነድፍም ምክንያት አድርጎ እናንተን የሚጣላበትን ሥራ አትሥሩ ሲል ፥ ርግብ የዋህ ናት በቀል ቂላትም እናንተም ኃዳግያነ በቀል ሁኑ ሲል በኖኅ ጊዜ ዋሻ መስኮት ከዘንዶ አፍ ገብታ በየውሃት ተጠብቃለች እናንተም በየውሃት ሆናችሁ ተጠበቃችሁ ኑሩ ሲል አንድም ከዕፀ ዘቄ ሥር ፀርፉ በየውሃት ትጠበቃለች እናንተም በየውሃት ተጠብቃችሁ ኑሩ ሲል ፥ ፀሐይ ልትሞቅ ስትወጣ በምዕራብ ሸምቆ ቆይቶ እያናቀ ይፈጃታል ። እናንተም በየውሃት ሁናችሁ መከራውን ተቀበሉ ሲል ።

፲፯ ወተዓቀቡ እምሰብእ እኩያን

፲፯ ከክፉ ሰዎች ተጠበቁ ።
እስመ ያገብኡክሙ ውስተ ሐፀዋዲት ።
አደርሱን ብለው ወደ ዐደባባይ ይወስዳችኋልና ፥
ወይቀሥፉክሙ በምኵራባቲሆሙ ።
በምኵራባቸው አግብተው ይገርፉችኋልና ፥

፲፰ ወይወስዱክሙ ኀበ መሳፍንት ወነገሥት በእንቲአየ ፥

፲፰ በስሜ ስለ አመናችሁ በስሜ ስለ ተጠራችሁ በስሜ ስለ አስተማራችሁ ወደ መኳንንተ አሕዛብ ወደ ነገሥተ አሕዛብ ይወስዷችኋልና ፥ ከመ ይኩን ስምዓ ላእሌሆሙ ዘእስራኤል መፈራረጃ ይሆንባቸው ዘንድ ፥ ምነው ያላመናችሁበት ይሏችዋል ምን አይተን እንመን ይላሉ ያውሳ በጸዓበ ደረት ባጭር ቁመት ተወስኖ ቢያስተምራችሁ ጡልታችሁ ተመቅኝታችሁ ስቅላችሁ የገደላችሁት ተብሎ ፥ አንድም ምነው ያላመናችሁበት ይሏቸዋል ምን አይተን እንመን ይላሉ ያውሳ ሐዋርያት የሱን ነገር ቢያስተምሯችሁ እንቀበላቸው ብላችሁ ለአሕዛብ ኄያሳለፉችሁ ቅሰጧቸው የነበረ ተብሎ ፥ ወላዕለ አሕዛብ ።
በአሕዛብም መፈራረጃ ይሆንባቸው ዘንድ ፥ ምነው ያላመናችሁበት ይሏቸዋል ምን አይተን እንመን ይላሉ ፥ ያውሳ ሐዋርያት የሱን ነገር ወረደ ተወለደ

[illegible] እንደቀበሉቻቸው በልቡ [illegible] በፍቅራቸው ፤ የቀልቀለት ጉበትኞቻቸው [illegible] የገዢ ተባሉ ።

፲፱ ወሶበ ያገብኡክሙ ኢተሐልዩ ዘትብሉ [illegible] ሉቃ ፲፪ ፡ ፲፩ ።

ኋላ [illegible] ባሉበት ጊዜ የምትናገሩትን [illegible] እንዲህ ቢሉን እንዲህ [illegible] እንመልሳለን ብላችሁ አታስቡ ። [illegible] በይእቲ ሰዓት ዘትትናገሩ ። የምትናገሩትን ፈጥኖ ይሰጣችኋል ማለት ። በጠየቋችሁ ጊዜ የምትመልሱት ይገለጽላችኋልና

፳ እስመ ኢኮንክሙ አንትሙ ዘትትናገሩ አላ መንፈሱ ለአቡክሙ ውእቱ ይትናገር በላዕሌክሙ ።

፳ የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁምና የአባታችሁ የእግዚአብሔር ሕይወቱ መንፈስ [illegible] ይናገራል እንጂ ።

[illegible] እንዲሁ ለሞት [illegible] ወእደውም ወንድሞ ቀሕማም [illegible] ይሰጣል [illegible]

[illegible]

፳፪ [illegible]

፳፪ [illegible] በኔ ስም ስለ ተጠ[illegible] እንደ ተጠላችሁ በሁሉ ዘንድ [illegible] ወዘሰ ተዐገሠ [illegible] የተቀበለ እሱ ይድናል እስከ [illegible] ይላል በዚያ እስከ ዕለተ ሞት መከራውን [illegible] የሚድን እሱ ነው ።

፳፫ ወሶበ ይሰድዱክሙ እምዛቲ ሀገር ጉዩ ውስተ ካልእታ ።

፳፫ ካንዱ አገር አስወጥተው ቢሰዷችሁ ወደ አንዱ አገር ሽሹ አማን እብለክሙ ኢይትፌጸማ አህጉረ እስራኤል እስከ ሶበ ይመጽእ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ካንዱ ወዳንዱ ስንል ያለ ክብር መቅረታችን አይደለምን ትሉኝ እንደሆነ ። ወልደ ዕጓለ እመሕያው እስኪ መጣ ማለት እኔ መጥቼ እስካድርባችሁ ድረስ የእስራኤል ዘነፍስ አገር አትፈጸምም ብዬ እንዳትፈጸም በውነት እነግራችኋለሁ ። አንድም ምድረ እስራኤል ጸባብ ናት በስምንት ቀን ትፈጸም የለምን ትሉኝ እንደሆነ ወልደ ዕጓለ እመሕያው እኔ እስክመጣ ጠባቢቱ ምድረ እስራኤል ቅሉ እንዳትፈጸም በውነት እነግራችኋለሁ ።

፳፬ አልቦ ረድእ ዘየዐቢ እምሊቁ ሉቃ ፮ ፡ ፵ ዮሐ ፲፫ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ፡ ፳

፳፬ በዚያውም ላይ ከመምህሩ የሚበልጥ ደቀ መዝሙር የለም ። ወኢገብርኒ ዘየዐቢ እምእግዚኡ ከጌታውም የሚበልጥ ባሪያ የለም ከሳኦል ዳዊት ከሐናንያ ቅዱስ ጳውሎስ ይበልጡ የለምን ቢሉ የጸጋ መብለጣቸው ባሉ አይደለም ።

፳፭ መጠኑ ለረድእ እምከመ ኮነ ከመ ሊቁ ።

፳፭ የደቀ መዝሙር መጠኑ እንደ መምህሩ ቢሆን ነው እንደ መምህሩ ቢሆን እንጂ ነው እንጂ መምህሩ ቢሆንበጉ ነው ። እንደ መምህሩ ቢሆን መጠኑ ነው ወለገብርኒ ከመ እግዚኡ ፤
የባሪያም መጠኑ እንደ ጌታው ነው እንደ ጌታው ቢሆን ነው እንደ ጌታው ቢሆን እንጂ ነው ፤ እንደ ጌታው ቢሆን መጠኑ ነው ።
ወሶበ ኮነ ለበዓለ ቤት በብዔል ዘቡል አፎ ፈድፋደ ለሰብአ ቤቱ ።
እምጸኢ ዓለማት ፈጣሬ ዓለማት እኔን በብዔል ዜቡል ያወጣቸዋል ካሉኝ እናንተንማ እንደምን አይሏችሁ።

፳፮ ኢትፍርህዎሙኬ እንከ ።
ማር ፬ ፡ ፳ ፡ ሉቃ ፰ ፡ ፲፯ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ።

፳፮ አትፍሯቸው ።
አልቦ ኅቡእ ክዱን ዘኢይትከሠት ወአልቦ ኅቡእ [illegible] ።
የማይገለጽና የማይታወቅ የለምና ማለት የናንተ ትርታንት የነሱ ደግነት ሳይገለጥ አይቀርምና ።

፳፯ ዘነገርኩክሙ በጽልመት ንግርዎ በብርሃን

፳፯ በጨለማ የነገርኋችሁን በብርሃን አስተምሩት ።
ወዘኒ እልኆሰስኩ ውስተ እዝንክሙ ሰብኩዎ በዲበ አንሕስት በጆሮዋችሁ የነገርኋችሁን በሰገነት ወጥታችሁ አስተምሩት ፤ ሐተታ ፤ ለመቶ ፳ ሰው ማስተማሩን በጨለማ በጆሮ መናገር ብሎ እንዲህ አለ ። አንድም ልጅነት ሳታገኙ የተማራችሁትን ልጅነት አግኝታችሁ አስተምሩት ልዕልና ነፍስ ሳታገኙ የተማራችሁትን ልዕልና ነፍስ አግኝታችሁ አስተምሩ ።

፳፰ ኢትፍርህዎሙ ለእለ ይቀትሉ ሥጋክሙ

፳፰ በሥጋችሁ የሚገድሏችሁን አትፍሯቸው
ወለነፍስክሙሰ ኢይክሉ ቀቲሎታ ።
ነፍሳችሁን መግደል አይቻላቸውምና ።
ወዑሑቱ ፍርህዎሰ ለዘእምድኅረ ቀተለ ዘቦ ሥልጣን ወይክል ነፍሰኒ ወሥጋኒ ነዊረ አኀጕሎ በውስተ ገሃነም ።
መፍራትስ ከገደለ በኋላ ነፍስና ሥጋን አዋሕዶ አሥኑሎ በገሃነም ፍዳ ያመጣ ዘንድ ሥልጣን ያለው እሱን ፍሩት ።

፳፱ አኮኑ ፪ቱ አዕዋፍ ይሠየጡ ለ፩ዱ ጸሪቀ አሶርዮን ።
እንዲህማ ከሆነ ወድቀን ወድቀን መቅረታችን አይደለም ተሉን እንደሆን ፬፣ ነገ፣ ፲፱፣ ፲፭ ።

፳፱ ግዕ፣ ፳፮፣ ፴፩ ። ሁለት አዕዋፍ በሁለት ሻሚ መሐለቅ ይሸጡ የለምን አሶርዮን የገበያ የሚዛን ስም ወአሐቲ እምኔሆን ኢትወድቅ ውስተ ምድር ዘእንበለ ያእምር አቡክሙ ሰማያዊ ።

ሰማያዊ አባታችሁ ሳያውቅ ከሁለቱ አንዲቱ አትወፋም በወጥመድ አትያዝም ።

፴ ወለክሙሰ ስእርተ ርእስክሙኒ ዅሉ ኁሉቍ ውእቱ ።

፴ እናንተስ የራሳችሁ ጸጕር ሳይቀር የተቈጠረ ነው የተቈጠረ እንዳይጠፋ አትጠፉም ።

፴፩ ኢትፍርህዎሙ እስመ እምብዙኃን አዕዋፍ ትኄይሱ አንትሙ

፴፩ ከተፈጥሮተ አዕዋፍ ተፈጥሮተ ሰብእ ይበልጣልና አይዟችሁ ። አንድም አኮኑ ብለህ መልስ በአራት በነቢያት ያሉ ሰዎች በሃይማኖት በጥምቀት ይኖሩ የለምን ወአሐቲ እምኔሆን ፣ በአራት በነቢያት ካሉ ሰዎች ሰማያዊ አባታችሁ ሳያውቅ አንዱ አይጠፋም ፣ ወለክሙሰ የናንተስ ደቀመዛሙርቶቻችሁ ሳይቀሩ የተቈጠሩ ናቸው ሥእርት አላቸው አርድእትን ጸጉር የራስ ጌጽ እንደሆነ ደቀ መዝሙር ለመምህሩ ጌጽ ነውና ጸጉር ያደገው ሲወድቅ ያላደገው ሲወጣ ደስ እንዲያሰኝ ደቀ መዝሙር ያጠናው ሲወጣ ያላጠናው ሲገባ ደስ ያሰኛልና ኢትፍርሆኬ በአራት በነቢያት ካሉ በሃይማኖት በጥምቀት ያላችሁ እናንት ትበልጣላችሁና አይዟችሁ አንድም አኮኑ ብለህ መልስ በሃይማኖት በጥምቀት ያሉ ሰዎች በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ይኖሩ የለምን ወአሐቲ እምኔሆን በሃይማኖት በጥምቀት ካሉ ሰማያዊ አባታችሁ ሳያወቅ አንዱ አይጠፋም ወለክሙሰ እንዳለፈው ኢትፍርሁ በሃይማኖት በጥምቀት ካሉ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ያላችሁ እናንተ ትበልጣላችሁና አትፍሩ ።

፴፪ ኵሉ ዘየአምን ብየ በቅድመ ሰብእ አነኒ እአምኖ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት ፣ ማር፡፰፣ ፴፰ ። ሉቃ ፣ ፱ ፣ ፳፮ ፣ ፲፪ ፣ ፰ ። ፪፣ ጢሞ ፣ ፪፡፲፪ ።

፴፪ በሰው ፊት ያመነብኝ ማለት ዘመን የወለደውን ንጉሥ የወደደውን ሳይል በሰው ፊት ያመነብኝን በሰማያዊ አባቴ ፊት ልጄ ወዳጄ እለዋለሁ

፴፫ ወለዘሰ ክህደኒ በገጸ ሰብእ አነኒ እክህዶ በገጸ አቡየ ዘበሰማያት ።

፴፫ ዘመን የወለደውን ንጉሥ የወደደውን ብሎ በሰው ፊት ያላመነብኝን ግን እኔም በሰማያዊ አባቴ ፊት ወለድኩህ ካድኩህ እለዋለሁ አንድም በቤተ ዮሴፍ ሲበላ ሲጠጣ አይቶ እሩቅ ብእሲ ነው ያላለኝን ልጄ ወዳጄ እለዋለሁ ። ከቤተ ዮሴፍ ሲበላ ሲጠጣ አይቶ እሩቅ ብእሲ ያለኝን ግን በሰማያዊ አባቴ ፊት ወለድኩህ ካድኩህ እለዋለሁ

፴፬ ኢይምሰልክሙ ዘአምጻእኩ ሰላመ ለብሔር

፴፬ ለሰው ፍቅርን አንድነትን ያመጣሁ አይምሰላችሁ ኢያምጻእኩ ይላል አላመጣሁም ።
አላ መጥባሕተ ።
ሰይፍን ነው እንጂ ማለት ጸብን ክርክርን መለያየትን ነው እንጂ ።

፴፭ ወመጻእኩሰ እፍልጥ ብእሴ እምአቡሁ

፴፭ ወንድ ልጅን ከአባቱ ።
ወወለተኒ እምእማ ።
ሴት ልጅን ከናቷ ።
ወመርዓተኒ እምሐማታ ።
መርዓትን ከማቷ ልለይ መጥቻለሁ እንጂ ፣ ሐተታ ፣ አማትና ምራት ሳይስማሙ ከመሬት አንዲሉ የማይስማሙ ያሉ አይደለምን ቢሉ በሚስማሙት መናገር ነው ። አንድም ወመጻእኩ እፍልጥ ብእሴ እምአቡሁ ብለህ መልስ ወንጌልን ከኦሪት ወወለተኒ ዐሠርቱ ቃላትን ከሥርዓተ ረበናት ወመርዓተኒ ነቢያት ካህናትን ከምኵራብ ልለይ መጥቻለሁ እንጂ አንድም ብእሴ እምአቡሁ ሰውን ከግብር አባቱ ከሰይጣን ፤ ወወለተኒ ፈቃደ ነፍስን ከፈቃደ ሥጋ ፣ ወመርዓተኒ ውሣጣዊት ግብርን ከአፍአዊት ግብር ልለይ መጥቻለሁ እንጂ ።

፴፮ ወሰብአ ቤቱ ይፃረር ለሰብእ

፴፮ ማር ፣ ፯ ፣ ፮ ። ሰውን ቤተሰቦቹ ይጣሉታል ዘመን የወለደውን ንጉሥ የወደደውን ይዞህ መሰለህ አትኖርም ይሉታል አንድም መከራ እቀበላለሁ ባለ ጊዜ ሐዋሳቱ ይፈሩበታል አንድም ሰብአ ቤቱ ይሁዳ ክርስቶስን ያሰቅለዋል ።

፴፯ ዘያፈቅር አባሁ ወእሞ እምኔየ ኢይደሉ ሊተ ወኢይክል ይፀመደኒ ። ሉቃ ፲፬ ፣ ፳፮ ።

፴፯ አባት እናት ከደዋል ልጆች አልካዱም ፤ በሃይማኖት እናት አባቴን ካልመሰልኩ ርስቱን ጉልቱን ለሌላ ያወርሱብኝ የለም ብሎ በሃይማኖት ጊዜ ከኔ ይልቅ አባት እናቱን የወደደ ሰው የኔ ደቀ መዝሙር ሊባል አይገባውም እኔን ሊያገለግለኝ አይቻለውም ።
ወዘያፈቅር ወልዶ ወወለቶ እምኔየ ኢይደሉ ሊተ ፤ አሁን ልጆች ከደዋል አባት እናት አልካዱም በሃይማኖት ልጆቼን ካልመሰልኳቸው ኋላ ማን ይረዳኛል ማን ያጠባኛል ብሎ በሃይማኖት ጊዜ ከኔ ይልቅ ልጆቹን የወደደ የኔ ደቀ መዝሙር ሊባል አይገባውም ወኢይክል ይፀመደኒ ።
ሊያገለግለኝ አይችልም

፴፰ ዘኢያጥብዕ ወዘኢነሥአ መስቀለ ሞቱ ወዘኢተለወኒ ኢይደልዎ ሊተ ።

፴፰ ወዘኒ ነፍሱን ከሥጋው የሚለይበትን መከራ ተቀብሎ በመከራ ከእመሰለኝ የኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይገባውም ።

፴፱ ዘረከባ ለነፍሱ ለይገድፋ ። ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፳፬ ፲፯ ፡ ፴፫ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ።

። [illegible] ጥቅም ያገኛት ሰውነቱን በሃይማኖት [illegible] ይጣላት ወዘኃደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ [illegible] ።

[illegible] የጣለት ሰውነቱን ይረከባ [illegible] ዘንድ ፳ድልት ብርሀት ሆና ያገኛታል እንድም ዘረከባ በሃይማኖት በጥምቀት ያገኛት ሰውነቱን በገሪነት መስቀል ይጣላት ። ወዘገደፋ በእንቲአየ [illegible] በገራህት መስቀል የጣላት [illegible] ያገኛታል ።

፵ ዘኪያክሙ ተወክፈ ኪያየ ተወክፈ

፵ ሉቃ ፡ ፰ ፡ ፲፮ ። ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ። እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ ማለት እናንተን በተቀበለ እኔ አድርብታለሁ ።

[illegible] ተወክፎ [illegible] ።

[illegible] ነቢይ ይነሥእ ።

፵፩ መምህሩን መምህር ብሎ የተቀበለ መምህሩ የሚያገኘውን እኔ የምሰጠውን ዋጋ ያገኛል ። ወዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ ዓስበ ጻድቅ ይነሥእ ። እውነተኛውን መምህር እውነተኛ መምህር ብሎ የተቀበለ መምህሩ የሚያገኘውን እኔ የምሰጠውን ዋጋ ያገኛል ። እንድም ዘተወክፈ ነቢየ ። ስለ አምላክ ኢሳይያስ ስለ አምላክ ኤርምያስ ብሎ ድኃውን የተቀበለ እኔ የምሰጠውን ነቢይ የሚያገኘውን ዋጋ ያገኛል ። ሀብተ ነቢይ እንዲሉ ። ወዘተወክፈ ጻድቀ ። ስለ አምላክ እንጦንስ ወመቃርስ ስለ አምላክ ተክለ ሃይማኖት ። ስለ አምላክ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ብሎ ድኃውን የተቀበለ ጻድቁ የሚያገኘውን እኔ የምሰጠውን ዋጋ ያገኛል ። ዝራዕ አክለከ ውስተ መቃብረ ጻድቃን ዕደው ጻድቃን የሀልዉ ውስተ ምሳሕከ ወለእመ እግረ ጻድቃን ሐፀበት እንዲል ፤ እንድም ነቢየ ያነሥእ ለክሙ ተብሎ የተነገረልኝ እኔን እውነተኛ የባሕርይ አምላክ ብሎ ያመነብኝ እኔ የምሰጠውን ዋጋ ያገኛል ። ወዘተወክፈ ጻድቀ ፤ ብእሲ ጻድቀ ዘጽድቀ ይነግረክሙ እንዲል እውነተኛ መምር የባሕርይ አምላክ ብሎ የተቀበለ እኔ የምሰጠውን ዋጋ ያገኛል ።

፵፪ ወዘአስተየ ዋሕደ እምእሉ ንኡሳን ጽዋዐ ማይ ቈሪረ ባሕቲቶ በስመ ረድእየ አማን እብለክሙ ኢይትኀጐል ዓስቦ

፵፪ ማር ፡ ፱ ፡ ፵ ፡ ቀሪር ፤ ይላል ንኡሳን የብዕል የተጣጣር ስለ አምላክ ጴጥሮስ ስለ አምላክ ጳውሎስ ብሎ በኔ ካመኑ ምእመናን ላንዱ ጽዋ ውኃ ያጠጣ ዋጋውን አያጣም ብዬ እንዳያጣ በውነት እነግራችኋለሁ ሐተታ ፤ ጠጅ ጠላ ሳለው አይደለም ባይኖረው ነው እንጂ ። ሳለውስ እንዳይገባ ለማጠየቅ አመቦ ብእሲ ዘቦ ዝክር ሠናይ ወያበውእ በግዓ ንውረ ርጉም ውእቱ ትላለች ኦሪት ካልጀመሩት አይሆንምና ዘአስተየ አለ ። እንድም ወርቁንም ዕንቁንም ጽዋዓ ማይ በማለት ተናገረው የመንግሥት በማይ ዋጋ አይሆንምና ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወሶበ ፈጸመ እግዚእ ኢየሱስ አዝዞቶሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ኃለፈ እምህየ ከመ ይምሀር ወይሰብክ ውስተ አህጉሪሆሙ ።

፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይኸን አስተምሮ ከፈጸመ በኋላ በየሀገራቸው ዞሮ ሊያስተምር ሔደ [illegible] ኢየሱስ ወበእንተ አርዳኢሁ ለዮሐንስ [illegible] ።

፪ ወሰሚዖ ዮሐንስ ምግባሮ ለእግዚእ ኢየሱስ እንዘ ሀሎ ቤተ ሞቅሕ ፈነወ ክልኤተ እምአርዳኢሁ ። ሉቃ ፯ ፡ ፲፰ ።

፪ ዮሐንስ መጥምቅ በግዞት ቤት ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን ታምራት ያስተማረውን ትምህርት የሠራውን ትሩፋት በሰማ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ወደሱ ላከ አካውህ እስጢፋኖስ ይባላሉ ።

፫ ወይቤሉ አንተኑ ዘትመጽእ ።

፫ ትመጣለህ ብለን ተስፋ የምናደርግህ አንተ ነህ ወቦኑ ባዕድ ዘንሴፎ ።

ወይም ይመጣል ፤ ብለን ተስፋ የምናደርገው ሌላ አለ ብሎ ሐተታ ፤ እሱ ተጠራጥሮ አይደለም እኒህ ተጠራጥረው ነበርና አይተው አምላክነቱን ይረዱት ብሎ ነው እንጂ ።

፬ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ሑሩ ወዜንውዎ ለዮሐንስ ዘርኢክሙ ወዘሰማዕክሙ ።

፬ ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት ለዮሐንስ ልቡናችሁ ንገሩት ።

፭ ዕውራን ይሬእዩ ። ኢሳ ፡ ፴፭ ፡ ፭ ፡ ፷፩ ፡

፭ ዕውራን ሥጋ በተአምራት ዕውራን ነፍስ በትምህርት ይድናሉ ሐንካሳን የሐውሩ ።

ሐንካሳን ሥጋ በታምራት ሐንካሳን ነፍስ በትምህርት ይድናሉ አለ ለምጽ ይነጽሑ ።

ዕውራነ ሥጋ በታምራት ዕውራነ ነፍስ በትምህርት ይድናሉ ወጽሙማን ይሰምዑ ።

ጽሙማነ ሥጋ በታምራት ጽሙማነ ነፍስ በትምህርት ይሰማሉ ወሙታን ይትነሥኡ ።

ሙታነ ሥጋ በታምራት ሙታነ ነፍስ በትምህርት ይነሣሉ ። ወነዳያን ይዜነዉ ።

ይብዕሉ ቢል ነው ነዳያነ ሥጋ በታምራት ነዳያነ ነፍስ በትምህርት ይከብራሉ ።

፮ ወብፁዕ ውእቱ ዘኢተዓቅፈ ብየ ።

ኔጋር ግን ሰውነቴን አይቶ ዕሩቅ ብእሲ ያላለኝ ንዑድ ክቡር ነው ። ሐተታ ፤ ጌታ ገልጾ አምላክ እኔ ነኝ አላላቸውም እንዳንድ ፈላስፋ አባቱ ሙቶ ያባቱን ቤተሰብና የሱን ቤተሰብ እያገዛ ሲኖር እየተጣሉ ቢያስቸግሩት ከፈላስፋ ሂዳችሁ ጠይቁልኝ ብሎ ልጆች ላከ ሂደው ቢነግሩት ዝም ብሎ ኋላ ከታክልት ቦታ ገብቶ የወራውን እየነቀለ ያልወራውን ፀሐይ እያሳቀረ ቆይቶ መጥቶ ተቀመጠ ። ይነግሩናል ብለው ቢያዩ የማይነግራቸው ሆነ ተመልሰው ሂዱ ምን አላችሁ አላቸው ። ቀንቶ ቢያየን ከመንገር በተቆጠረ ነበር አሉት ። ያውቀስታልዋ ምን ሲያደርግ ነበር አላቸው ። ሂደን ብንነግረው ዝም አሰኘ ኋላ ከተክል ቦታ ገብቶ የወራ የወራውን ነቅሎ ያልወራውን በፀሐር እያስቃቀለ ቆይቶ ተመልሶ ተቀመጠ ። ይነግረናል ብለን ብናይ የማይነግረን ሆኖ መጣን አሉት ። እናንተ ባታውቁት ነው እንጂ እሱስ ነግሯችኋል ፤ የወራውን መንቀሉ ያባትህን ቤተሰብ አሰናብት ሲልህ ነው ። ያልወራውን ፀሐር ማስታቀፉ ያንተን ቤተሰብ ግዛቸሁ ኑር ሲለኝ ነው ብሎ ያባቱን ቤተሰብ አሰናብቶ የሱን ቤተሰብ እየገዛ በጤና የሚኖር ሆኖዋል ። እንደዚህም ሁሉ ያ ሥራ ሠርቶ አሳያቸው እንጂ ገልጾ እንዳልነገራቸው ጌታም ታምራት አድርጎ አሳያቸው እንጂ ገልጾ አምላክ እኔ ነኝ አላላቸውም ።

ዘከመ ወደሶ እግዚእ ኢየሱስ ለዮሐንስ መጥምቅ ።

፯ ወሶበ ኃለፉ እሉ ላእካነ ዮሐንስ አኀዘ ይበሎሙ ለሕዝብ በእንተ ዮሐንስ መጥምቅ ። ሉቃ ፯ ፣ ፳፬ ።

፯ ከዮሐንስ ተልከው የመጡት ከሄዱ በኋላ የዮሐንስ መጥምቅን ነገር ለሕዝቡ ይነግራቸው ጀመር ። ዮሐንስ መላኩ ተጠራጥሮ እንዳይደለ ሄደው ይረዱት ብሎ እንደ ሆነ ፤ ሳሉ አለመናገሩ ከሄዱ በኋላ መናገሩ ስለምን ቢሉ ሳሉ ነግሯቸው ቢሆን አመስግኖ ቢልከበት አመስግኖ ላከበት ባሉ ነበርና ።

፰ ምንተኑመ ወፃእክሙ ገዳመ ትርአዩ ።

፰ በገዳም ምን ልታዩ ወጣችኋል ፤ ብርዓ ፤ ዘይትሀወስ እምነፋስ ። ነፋስ የሚወዘውዘው መቃ መሰዩን ልታዩ ወጣችኋል ። ወሚመ ብእሴ ዘርሡይ ልብሰ ቀጠንት ለቢሶ ። ወይም ረፈአ ግምጃ የለበሰን ልታዩ ወጣችኋል ። እለሰ ቀጠንተ ይለብሱ ውስተ አብያተ ነገሥት ሀለው ።

ግምጃ የለበሱ በነገሥታት ቤት በገዳም አሉ ። ረፈአ ግምጃ የለበሰ በገዳም እንዴምን ይገኛል ቢሉ ነገሥታት መኳንንት ተድላ እናድርግ ባሉ ጊዜ ገዳም ወጥተው ድንኳን አስጥለው ድንኳን አስተክለው ይውላሉ በዚህ ጊዜ ብዙ ባለፀጎች አጊጠው ይታያሉና ። አንድም ምንተኑመ ብሎ መልስ ፤ መቃ መሰዩን ነፋስ አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ አንድ ጊዜ ወደ ግራ እንደሚወዘውዘው የናንተም ልቡና አንድ ጊዜ የባሕርይ አምላክ ፤ አንድ ጊዜ ዕሩቅ ብእሲ ነው ይላል ። ዮሐንስም አንድ ጊዜ ዕሩቅ ብእሲ አንድ ጊዜ የባሕርይ አምላክ ይላልናልና ብላችሁ ወጣችኋል ወሚመ ብእሴ ሌት ከቀን ግምጃ እንዲለዋወጥ የናንተም ልቡና አንድ ጊዜ የባሕርይ አምላክ አንድ ጊዜ ዕሩቅ ብእሲ በማለት ይለዋወጣል ። ዮሐንስም አንድ ጊዜ የባሕርይ አምላክ አንድ ጊዜ ዕሩቅ ብእሲ በማለት ይለዋወጣል ብላችሁ ወጣችኋል ። አንድም መልስ ፤ መቃ መሰዩን ነፋስ አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ አንድ ጊዜ ወደ ግራ እንዲለው ዮሐንስም አንድ ጊዜ ዕሩቅ ብእሲ አንድ ጊዜ የባሕርይ አምላክ ይላል ብላችሁ ወጣችኋል ፤ ወሚመ ፤ ሌት ከቀን ግምጃ እንዲለዋወጥ ዮሐንስም አንድ ጊዜ የባሕርይ አምላክ አንድ ጊዜ ዕሩቅ ብእሲ በማለት ይለዋወጣል ብላችሁ ወጣችኋል ። እለሰ ፤ የቤቱን ለማድ የማታውቁን ልብስ የሚለዋወጡ እራት እሳቦች በነገሥታት ቤት አሉላችሁ ።

አንድም ለምንት ወፃእክሙ ትርአዩ ገዳመ ቢል ። ወደ ገዳም ታዩ ዘንድ ለምን ወጣችኋል ፤ ብርዓ ፤ ነፋስ የሚወዘውዘው መቃ መሰዩን ልታዩ ወጣችኋልን ልታዩ ወጣችኋል ልታዩ ወጣችኋል ። ወሚመ ብእሴ ፤ ረፈአ ግምጃን የለበሰን ልታዩ ወጣችኋልን ልታዩ ወጣችኋል ልታዩ ወጣችኋላ ፤ ረፈአ ግምጃ የለበሱስ በነገሥታት ቤት አሉ ።

፱ ወምንተኑመ ወፃእክሙ ትርአዩ ።

፱ ምን ልታዩ ወጣችኋል ። ነቢየ ።

ነቢይን ልታዩ ወጣችኋል ። እወ እብለክሙ ወፈድፋደ የዓቢ እምነቢያት ።

አዎን ትሰሙኝ እንደሆነ ዮሐንስ ከነቢያት ይበልጣል ብዬ እንዲበልጥ በእውነት እነግራችኋለሁ ።

፲ እስመ ዝንቱ ውእቱ ዘበእንቲአሁ ተጽሕፈ ናሁ አነ እፌኑ መልአኪየ ቅድመ ገጽከ ዘይጼይሕ ፍኖተከ በቅድሜከ ፡ ሚልክ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ማር ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ሉቃስ ፡ ፯ ፡ ፳፯ ።

፲ በፊትህ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛየን እነሆ በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተነገረለት ይህ ዮሐንስ ነውና በሌላው አልቦቱ መልአክ ለመልአክ ይላል ። ከዚህ እንዴህ አለ እንደምነው ቢሉ ለሌላው እውነት ነው እሱ ግን ትንቢት ተነገሮለታልና ።

፲፩ አማን እብለክሙ ኢተንሥአ እምትውልደ አንስት ዘየዓቢ እምዮሐንስ መጥምቅ ።

፲፩ ሴቶች ከወለዷቸው ወገን ከዮሐንስ መጥምቅ የሚበልጥ አልተነሣም ብዬ እንዳልተነሣም በእውነት እነግራችኋለሁ ፤ ስሕተት በሕይወት [illegible] እምትውልደ አንስት እኽ ። ወበመንግሥተ ሰማይስ ዘይንእስ የዓብዮ ።

መንግሥተ ሰማይ ሆና በመስጠት ግን መንፈቅ የሚያንሰው ጌታ ይበልጠዋል ፤ አንድም ወደ መንግሥት ሰማይ በማግባት ከመንግሥት ሰማያት በማውጣት ግን ደቂቅ መዘሙሩ ዮሐንስ ወንጌላዊ ይበልጠዋል ለዚያ ሥልጣን ክህነት አለው ። ለዚህ ግን ሥልጣን ክህነት አልነበረውምና ።

፲፪ እምአመ መዋዕሊሁ ለዮሐንስ መጥምቅ እስከ ዛቲ ዕለት ትትገፋዕ መንግሥተ ሰማያት ።

፲፪ የዮሐንስ መጥምቅ ማስተማር ከጀመረበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማይ ወንጌል የሚቀበላት አጥታ ትበደላለች ።

ወመፍቀዳን ይትመሰጥዋ ።

ግፍ ወገፋዐ ልበደ ሥራ የነበሩ ሐዋርያት ይቀበሏታል ገፋዕያን ይላል ሰውን በግብር ምክንያት ይበድሉ የነበሩ እነ ማቴዎስ እነ ዘኬዎስ ይቀበሏታል ። ይትመሰጥዋ ማለቱ ግን የወደዱትን ምግብ እየተሻሙ እንዲመገቡት ወደው ይቀበሏታል ። ቤል ነው አንድም ወእመዋዕለ ዮሐንስ ብለህ መልስ ዮሐንስ ማስተማር ከጀመረበት ቀን ጀምሮ መንግሥት ሰማያት የሚወርሳት አጥታ ተበድላ ትኖራለች ወመፍቀዳን በንስሐ የሚበድሉ ምእመናን ፤ ገፋዕያን ይላል ሰውን በንስሐ የሚበድሉ ቀሳውስት ይወርሷታል ።

፲፫ እስመ ኵሎሙ ነቢያትኒ ወኦሪት እስከ ዮሐንስ ተነበዩ ።

፲፫ ኦሪትም ነቢያትም ሁሉ እስከ ዮሐንስ ድረስ አስተምረዋልና

፲፬ ወእመሰ ትፈቅዱ ትትወከፍዎ ዝ ውእቱ ኤልያስ ዘሀለዎ ይምጻእ ።

ናሁ አነ እፌኑ መልአኪየ ተብሎ የተነገረ ለኤልያስ ነው እንጂ መቼ ለዮሐንስ ነው እንዲሉት በውቀ ሊሞቁ እንዲሉትም ዐውቆ ማምጣት ልማዱ ነው እንዳይሉም በሌላ ምዕራፍ ፳ ፥ ቍ ፡ ፲፪ ። ሚል ፡ ፬ ፡ ፭

፲፬ ልትቀበሉትስ ከወደዳችሁ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ዮሐንስ ነው ። ሐተታ ዮሐንስ ኤልያስን በምን ይመስለዋል ቢሉ ኤልያስን እንጂ ይለዋል ዮሐንስንም ዘልብሱ ፀጉረ ገመል ይለዋልና ። ኤልያስን ጸዋሚ ተሐራሚ ዝጉሐዊ ባሕታዊ ይለዋል ዮሐንስንም ጸዋሚ ተሐራሚ ዝጉሐዊ ባሕታዊ ይለዋልና ኤልያስ መገሥጸ አክዓብ ወኤልዛቤል እንደሆነ ዮሐንስም መገሥፀ ሄሮድስ ወሄሮድያዳ ነውና ፤ ኤልያስ ለደኃራዊ ምጽአቱ መንፈቅ ተቀድሞ እንዲያስተምር ዮሐንስም ለቀዳማዊ ምጽአቱ መንፈቅ ተቀድሞ አስተምሯልና ።

፲፭ ዘቦ እዝን ሰሚዐ ለይስማዕ ።

፲፭ [illegible] ኤልያስ እንዳይደለ ዮሐንስ እንደሆነ እዝን ልቡና ያለው ይስማ

፲፮ በምንት አስተማስሎ ለዝንቱ ትውልድ

፲፮ ቤተ አይሁድን በምን እመስላቸዋለሁ ምሳሌ ቢያጣላት አንድም ይመስሉ ደቂቅ ለማለት ።

ይመስሉ ደቂቅ እለ ይነብሩ ውስተ ምሥያጥ ።

ከደበባይ የተቀመጡን ።

ወይጼውዑ ቢጾሙ ።

ባልንጀሮቻቸው የሚጠሯቸውን ።

፲፯ ወይብልዎሙ እንዘርንጽክሙ ወኢዘፈንክሙ

፲፯ የዘፈን ዜማ ቀነቀንላችሁ አልተቀበላችሁንም ።

አስቆቀውነ ለክሙ ወኢበከይክሙ ።

የለቅሶ ዜማ ቀነቀንላችሁ አልተቀበላችሁንም የሚሉ ልጆችን ይመስላሉ ።

፲፰ እስመ መጽአ ዮሐንስ እንዘ ኢይበልዕ ወኢይሰቲ ወይቤልዎ ጋኔን ቦቱ ።

፲፰ ዮሐንስ ሳይበላ ሳይጠጣ ቢያስተምር የማያበላ የማያስጠጣ ጋኔን አድሮበታል ብላችሁታልና አስቆቀውነ ላለው ።

፲፱ ወመጽአ ወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዘ ይበልዕ ወይሰቲ ወይቤልዎ ነዋ ብእሲ በላዒ ወሰታዬ ወይን አርከ መጸብሓን ወኃጥኣን ።

፲፱ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ እየበላ እየጠጣ ቢያስተምር መብል መጠጥ ወዳጅ የኃጥአን የመጸብሓን ወዳጅ ብላችሁታልና ። እንዘርንክ ለክሙ ላለው ። ሐተታ፡ ሕፃናቱ አራቱ ያታ ናቸው አንዱ ያታ የዘፈን ዜማ ቀነቀኑ አንዱ ያታ ተቀበሉ አንዱ ያታ ዝም አሉ በዳር ያሉ አንዱ ያታ እኒያ ሲቀበሉ እኒህ ዝም ማለታቸው ደስ ባይላቸው እንጅ ነው ብለው የልቅሶ ዜማ ቀነቀኑ የተቀበሉ ተቀበሉ ያልተቀበሉ ዝም አሉ ። የዘፈን ዜማ የቀነቀኑ አርድእት ክርስቶስ የተቀበሉ ኃጥአን መጸብሓን ያልተቀበሉ ጸሐፍት ፈሪሳውያን የልቅሶ ዜማ

የቀንቀኑ አርድእተ ዮሐንስ ፤ አንድም ምስቁ ማታ ናቸው፣ አንዱ ጋታ የዘፈን ዜማ ቀንቀኑ አንዱ ጋታ ተቀበሉ አንዱ ረታ ዝም አሉ እኒህ ሲቀበሉ እኒያ ዝም ማለታቸው ደስ ባይላቸው እንጅ ነው ብለው የዘፈን ዜማ የተቀኙትን መልሰው የልቅሶ ዜማ ቀንቅነዋል የተቀበሉ ተቀበሉ እንቀበልም ያሉ ዝም አሉ የተቀበሉ ኃጥአን መጽሐፍን እንቀበልም ያሉ ጻሐፍት ፈሪሳውያን የጌታን ትምህርት በዘፈን የዮሐንስን በልቅሶ መስሉ ተናገረ በለምን ቢሉ በጌታ ትምህርት ታምራት ተደርጎበታል ልጅነት ተገኝቶበታል ። በዮሐንስ ትምህርት ግን ልጅነት አልተገኘበትም ታምራት አልተደረገበትምና ምነው ያውስ ቢሆን የዮሐንስ ቀድሞ የጌታ አይከተልም ነበር ቢሉ የጌታ ቃል ሳለ የባሪያ ቃል እናስቀድምም ብለው በብያኔ አስተደመውታል ነገር ግን ሁሉም አንድ ነው ። ዮሐንስ ሳይበላ ሳይጠጣ ማስተማሩ ታምራት መስሏቸው ይሳቡ እንደ ሆነ ብሎ ፣ ጌታ እየበላ እየጠጣ ማስተማሩ በፍቅር ለመሳብ ነው ። ከዚያም በያማምሩ ከዚያም በያጠምሩ ለመያዝ እንደሆነ ።

ወጸድቀት ጥበብ እምደቂቃ ወእምግባራ ።
ጥበብ ወልድ ከሥራዋ ከልጆቹዋ የተነሣ ከበረች ጸድቀት እምኔየ ትዕግር እንዲል እንድም ደቂቃ በምግባሯ በሥራዋ ልጆቹዋን ረታች ጸድቀተኒ ትዕግር እንዲል እንድም ጥበብ ወልድ ከልጆቹዋ ይልቅ በሥራዋ ከበረች ።

ዘከመ ጌሰን ፤

ለአህጉር ኢነሳሕያት ።

፳ ወእምዝ አኀዘ እግዚእ ኢየሱስ ይጌሰን ለአህጉር እለ በውስቴቶን ገብረ ኃይለ ብዙኀ ።

፳ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ደጋግ ታምራት ያደረገባቸውን ምኩራባት ይነቅፋቸው ጀመር።
እስመ ኢነስሑ ።
አላመኑምና ።

፳፩ ወይቤሎን አሌ ለኪ ኮራዚ
፳፩ ስመ ምኩራብ ነው ኮራዚ ወዮልሽ አያለ
ሉቃ ፣ ፲ ፣ ፲፫ ። አሌ ለኪ ቤተ ሳይዳ ።
ቤተ ሳይዳ ወዮልሽ ።
እስመ ሶበ በጢሮስ ወበሲዶና ተገብረ ኃይል ዘተገብረ በውስቴትክን ።
በናንተ የተደረገው ታምራት በጢሮስ በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ።
እምነስሑ በሐመድ ።
ማቅ ለብሰው አመድ ነስንሰው ንስሐ በገቡ ነበር ።
ሐተታ፤ በጢሮስ ኪራም ፳፪ ዘመን ኑሮ የለምን በሲዶናስ ኤልያስ አንድ ምውት ኤልሳዕ ሁለት ምውት አስነሥቶ የለም ቢሉ በኒያ ሕጸጽ አለበት በጌታ ግን ሕጸጽ የለበትምና የኒያ የጸጋ ነው የጌታ ግን የባሕርይ ነውና ።

፳፪ ወባሕቱ እብለክሙ ጢሮስ ወሲዶና ይረክባ ሣሕተ ፈድፋደ እምኔክን አመ ዕለተ ደይን ።

፳፪ ነገር ግን ጢሮስ ሲዶና በፍርድ ቀን ክናንተ ይልቅ ዕረፍትን ያገኛሉ ፣ ብየ እነግራችኋለሁ ።

፳፫ ወአንቲኒ ቅፍርናሆም ለእመ እስከ ሰማይ ትትሌዓሊ እስከ ሲኦል ትወርዲ ።

፳፫ አንቺም ቅፍርናሆም እስከ ሰማይ ብትደርሺ እስከ ሲኦል ትወርጂ ዘንድ አለሽ ። አንቺም ቤተ አይሁድ ክርስቶስን ዕሩቅ ብእሲ እስከ ማለት ብትደርሺ ገሃነም ትወርጂ ዘንድ አለሽ ።
እስመ ሶበሁ ተገብረ ኃይል ዘተገብረ በውስቴትኪ እምሀለወት እስከ የም ።
ባንቺ የተደረገ ታምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን ንስሐ ገብታ ከተፈረደበት ፍርድ ድና እስከሁን ፀሐይወት በኖረች ነበር ። ሐተታ ፣ በሰዶም ሎጥ በእንግዳ ደረቅ ዕንጨት አለምልሟል መላእክትን ስ ዕንግድነት ተቀበሉ የለም ቢሉ የሱ የጸጋ ነው የጌታ ግን የባሕርይ ነውና ፣ በሱ ሕጸጽ አለበት በጌታ ግን ሕጸጽ የለበትምና ።
፳፬ ወባሕቱ እብለክሙ ከመ ምድረ ሰዶም ሣሕተ ትረክብ ፈድፋደ እምኔኪ አመ ዕለተ ደይን ።
፳፬ ነገር ግን በፍርድ ቀን ካንቺ ይልቅ ሰዶም ዕረፍትን ታገኛለች ብየ እነግራችኋለሁ ።
፳፭ ወይእተ ጊዜ አውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤ እእምነከ አባ እግዚእ ሰማያት ወምድር ።
ሉቃ ፣ ፲፩ ፣ ፩ ።
በዚህ ያልተያዘ በሉቃስ የተያዘ ነው ። ሰብዓ አርድእት መጥተው አጋንንት ገረሩ ለነ በስምከ ብለውታል እነሱ ማመስገን ባይቻላቸው በዓቸው ተገብቶ ያመሰግንላቸዋል ።
፳፭ ያን ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዩን ምድሩን የፈጠርህ አባቴ አመሰግንሃለሁ አለ ወልድየ እሙና እንዲል አእኮቶ ሲል ።
ዘኀባእኮ ለዝንቱ እምጠቢባን ወማእምራን ወከሠትኮ ለሕፃናት ።
የኔን እምላክነት ዐዋቆች ነን ከሚሉ ከጸሐፍት ከፈሪሳውያን ሰውረህ ለሕፃናት ለአእምሮ ለሐዋርያት የገለጥኸው ።
፳፮ እወ አባ እስመ ከመዝ ኮነ ሥምረትከ በቅድሜከ ።
፳፮ እዎን አባቴ አዋቂ ነን ከሚሉ መሰወር አላዋቂ ነን ለሚሉ መግለጥ ቀድሞም ልማድህ ነው፤ ምሥጢረ ድኅነትን ከሰብአ ትካት ሰውረህ ለኖኅ ከሰብአ ሰዶም ሰውረህ ለሎጥ እንደገለጥህ ።
፳፯ ኵሉ ተውህበኒ እምኀበ አቡየ ።
ዮሐንስ ፫፥፴፭ ። ፭ ፣ ፳፫ ፣ ፳፱ ። ፰ ፣ ፲፱ ። ፲ ፣ ፲፭ ።

፳፯ ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጠኝ ። የተሰጠውስ በማኅፀን ሲዋሐድ ነው፣ ወለዘፈቀደ ወልድ ይክሥት ሎቱ ለማለት ነው እንጂ

ወአልቦ ዘየአምሮ ለወልድ ዘእንበለ አብ
አብን ወላዲ ካላለ ወልድን ተወላዲ ብሎ የሚያምን የለም ።
ወአልቦ ዘየአምሮ ለአብ ዘእንበለ ወልድ ።
ወልድን ተወላዲ ካላለ አብን ወላዲ ብሎ የሚያምን የለም አንድም አብ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ባይመሰክርለት ወልድን የሚያውቀው አልነበረም ። ወአልቦ ፣ ወጸአኩ እምኀበ አብ ወመጻእኩ አቡየ ፈነወኒ ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ ብሎ ሳይመሰክር አብን የሚያውቀው አልነበረም ፣ አንድም ፣ ከአብ በቀር አብ ያውቀዋል እንጂ ያለ አብ ወልድን በባሕርዩ የሚያውቀው የለም ፣ ወአልቦ ፣ ከወልድ በቀር ወልድ ያውቀዋል እንጂ ያለ ወልድ አብን በባሕርዩ የሚያውቀው የለም ።
ወለዘፈቀደ ወልድ ይክሥት ሎቱ ።
ወልድ ሊገልጽለት ለወደደው ይገልጽለታል ፈቀደ ለሁለቱም ።

፳፰ ንዑ ኀቤየ ኵልክሙ ስሩሃን ወክቡዳን ጾር
፳፰ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደኔ ኑ ማለት በጾመ አርባ በጾመ ኃጢአት የደከማችሁ ጾረ ገቢር የረበናት ትብትብ ያለባችሁ በኔ እመኑ ፣

፳፱ ወአነ አዐርፈክሙ ። ኤር ፣ ፮ ፣ ፲፮ ፣ ዮሐንስ ፣ ፳ ፣ ፫ ።
ዕረፍተ ነፍስ ሰጥቼ አሳርፋችኋለሁ ።

፳፱ አብነት ንሥኡ ጾሩ ይላል ። ቀንበሬን ተሸከሙ ማለት ሕጌን ያዙ ። ሐተታ ቀንበር አላት ወንጌልን ቀንበር ሁለቱን በሮች አንድ አንድታ ደርግ ወንጌልም ሕዝብና አሕዛብን አንድ ታደርጋለችና ።
ተመሀሩ ወአእምሩ እምኔየ ከመ የዋህ አነ ወትሑት ልብየ የዋህ ትሑት እንደሆንኩ መጠን ከኔ ተምራችሁ ዕወቁ ። ወትረክቡ ዕረፍተ ለነፍስክሙ ዕረፍተ ነፍስ ታገኛላችሁ ።

፴ እስመ አርዑትየኒ ሠናይ ።
፴ ቀንበሬ ልዝብ ነውና ።
ወጾርየኒ ቀሊል ።
ሸክሜ ቀሊል ነውና ።
ሕጌ ወንጌል ደግ ሕግ ናትና፣ትእዛዜም ቀሊል ነውና ከዚህ የከበደን አለ ለዚህ ጸፍአከ መልታሕቲከ ዘየማን ሚጥ ሎቱ ካልዕታሂ ወለዘሂ አበጠከ አሐደ ምዕራፈ ሑር ምስሌሁ ፪ተ ወለዘሂ ይፈቅድ ይትዓገልከ መልበስከ ኅድግ ሎቱ ክዳንከሂ ትላለች ከዚህ የከበደ ምን አለና እንዲህ አለ ቢሉ አደርጋዋለሁ በሚል ዘንድ ቀሊል ነውና ፣ አንድም ለወጣኒያን ክቡድ ቢሆን ለፍጹማን ቀሊል ነውና ፣ አንድም ፣ ከሕገ ኦሪት ሲለይ ነው ፣ ኦሪት ወገሩ ሰቀሉ ብላ ካስናበተች በኋላ [illegible] ወንጌል ግን በንስሐ ትላለችና ፣

ንስሐውን ቅሉ ሰብዓ በሰብዐ ትላለችና ፣ ሕገ መሲሐዊት ተራገርኋት እንጂል ፣ አንድም ኦሪት ፈጽማችሁ ጽድቁ ትላለች ፣ ወንጌል ግን በክርስቶስ ፈጻሚነት ትላለችና ፣ አንድም ከሕገ አረሚ ሲለይ ሕገ አረሚ ላህምል ግልቀ ሠውዕ ሰብአ ትላለች በወንጌል ግን ይህ ሁሉ የለምና ፣ ከሕገ አሕዛብ ሲለይ አሕዛብ ከዱር ገብተው ዛፉን ቆርጠው ክፉ እግር ሲያወጡ ቀለሙን ግድፉን ሲያከናውኑ ድካም ጸለበትና

ምዕራፍ ፲፪ ።

በእንተ ሰዊት ።

፩ ወበውእቱ መዋዕል ወፈረ እግዚእ ኢየሱስ በሰንበት እንተ ማዕከለ ገራውህ ። ማር ፪ ፣ ፳፫ ፣ ሉቃ ፣ ፮ ፣ ፩ ።

፩ በዚያ ወራት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዳሜ በእኽል መካከል ሄደ ።
አርዳኢሁሰ ርኅቡ ወአኀዙ ይምሀዉ ሰዊተ ወይብልዑ ፣ ፪ ደቀ መዛሙርቱ ግን ተርበው ነበርና እሸት እያሹ ይበሉ ጀመር ።
፪ ወርእዮሙ ፈሪሳውያን ይቤልዎ ርኢ ዘይገብሩ አርዳኢከ ዘኢይከውን ገቢረ በሰንበት ።
፪ ፈሪሳውያን ሰምተው ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ሊሠሩት የማይገባ ሥራ ሲሠሩ አስተውል አሉት ።
፫ ወይቤሎሙ ኢያንበብክሙኑ ዘገብረ ዳዊት አመ ርኅበ ።
፫ ዳዊት በተራበ ጊዜ ያደረገውን አልተመለከታችሁም አላቸው ።
ውእቱኒ ወእለ ምስሌሁ ።
እሱም ከሱ ጋራ ያሉ ብላቴኖቹ ያደረጉትን ።
፬ ዘከመ ቦአ ቤቶ ለእግዚአብሔር ወበልዓ ሕባውዘ ቍርባን ዘኢይከውኖ ለበሊዕ ።
፬ ከቤተ እግዚአብሔር ገብቶ ሊበላው የማይገባውን መሥዋቱን እንደበላ ።
ወኢ ለእለ ምስሌሁ ።
ከሱም ጋራ ያሉ ሊበሉት የማይገባውን ።
ዘእንበለ ለካህናት ለባሕቲቶሙ
ለካህናት ብቻ ይገባቸዋል እንጂ ።
፭ ወካዕበ ኢያንበብክሙኑ ዘሀሎ ውስተ ኦሪት ከመ ካህናት እለ ውስተ ቤተ መቅደስ ያረኩስዋ ለሰንበት ። ዘሌ ፳፬፣፰ ፣ ዘኍ ፳፰ ፣ ፱ ።
፭ ይስዕርዋ ሲል ነው ። በቤተ መቅደስ ያሉ ካህናት ቅዳሜን እንዲሽሯት በኦሪት የተጻፈውን አል

ሕይወቴ መንፈስ ቅዱስ ለህልውና የመረጠችው ወዳጄ ።

ወእነብር መንፈስየ ላዕሌሁ ።
ሕይወቴ መንፈስ ቅዱስን ሕይወት የማደርግለት።

፲፰ ውእቱ ይሜህር ፍትሕየ ለአሕዛብ ወኮነኒየ ለሕዝቢ ።

፲፰ እሱ ሃይማኖተ ወንጌልን ለአሕዛብ ሃይማኖተ ኦሪትን ለእሥራኤል ሲያስተምር ።

ኢይደምፅ ወኢይጸርኅ ።
አይሰማም ፤ ወአልቦ ዘይሰምዖ ቃሎ በምሥራብት።በምሥራባት ሲያስተምር የሚሰማው የለም ተብሎ በኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ። ሐተታ በዮሐንስ ወዓልዓለ ቃሎ በምሥራብ ይላል በዚህ እንዲህ አለ አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ዮሐንስ ነው ለስሞቱ ነው የሚያስተምር ፤ ከዚህ እንዲህ ማለቱ ውዳሴ ከንቱ አይሰማበትም ቢል ነው ።

፳ ብርዐ ቅጥቁጥ ኢይሰብር ፤

፳ ከእግሩ ጭምትነት የተነሣ እስኪሉ የወጣለት የፀንቁላል ቅርፍት አይደቅበትም ።
ወሡፀ ዘይጠይስ ኢይጠፍዕ ከቃሉ ልዝብነት የተነሣ የሚጤያጤስ የጧፍ ኩስታሪ አይጠፋበትም
እስከ ይገብእ ፍትሐ መዊኦቱ
አሸናፊ ፍርዱ በአይሁድ በአጋንንት እስኪመለስ ድረስ ።

፳፩ ወበስሙ ዚአሁ ይትአመኑ አሕዛብ ።

፳፩ አሕዛብም በስሙ እስኪያምኑ ድረስ ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ተግኅሠ እምሀየ ። አንድም በንስሐ በኀዘን የሚቀጠቀጥ በተስፋ የሚጤያጤስ ጻድቅም አይጠፋም በዕለተ ዓርብ አሸናፊ ፍርዱ በአጋንንት እስኪ መለስ ድረስ አሕዛብ በስሙ እስኪያምኑ ድረስ ብሎ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ። እሕየዎሙ ። ሞቶ ሥጋው ለሞተ ነፍሱ ምልክት እንደሆነ ድኅነተ ሥጋውም ለድኅነተ ነፍሱ ምልክት ነውና ። አንድም በቅንዓት የሚቀጠቀጥ በቅንዓት የሚጤያጤስ አይሁዳዊ አይጠፋም ። አሸናፊ ፍርዱ በአይሁድ በ፵ ዘመን እስኪ መለስ ድረስ ። አሕዛብም በስሙ እስኪያምኑ ድረስ ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ፤ ተማከሩ ይቅትልዎ ፤ አንድም መቃ መስየ የፍግ እሳት ወንጌል አትጠፋበትም አሸናፊ ፍርዱ በአይሁድ በአጋንንት እስኪመለስ ድረስ ፤ አሕዛብም በስሙ እስኪያምኑ ድረስ ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ።

ገሠፆሙ ሐተታ ፤ መቃ መስየ እሳት ወንጌልን ፤ መቃ መሰየ በጋውን ማንም ሲጠቀጥቀው ይባጃል ። ክረምት በሆነ ጊዜ በያለበት ያፈላል ወንጌልም ስትነገር አንድ ሰው በሰማዕትነት ይሞታል ታምራት ይደረጋል ብዙ ሰው ያምናል ። የፍግ እሳት ካንድ ላይ ያቃጠሉት እንደሆነ ሁለተኛ ምክትኛ እቃጥሉኝ አይልም ተያይዞ ይነዳል ወንጌልም በመቶ ሐያ ቤተሰብ ተጀምራ እስከ ምጽአት ድረስ ስትነገር ትኖራለችና ።

እንድም ብርዓ ቅጥቁጠ ኢይሰብር ወሡዓ ዘይጠይስ ኢይጠፍዕ ይላል እብሎት ለቀው ያጠፋችኋል ቢሏቸው ስንኳን እኛን ሊያጠፉ እስኪሉ የወጣለት የፀንቁላል ቅርፍትስ እንኳ አያደቅም ። የሚያጤያጤስ የጧፍ ኩስታሪስ እንኳ አያጠፋም ይሉታል ብሎ ኢሳይያስ የተናገረው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ፈለሰ እምህየ ።

በእንተ ዕውር ወጽሙም

ዘቦቱ ጋኔን ።

፳፪ ወእምዝ አምጽኡ ኀቤሁ በጋኔን ዕውረ ወጽሙመ ወበሐመ ፤

፳፪ ከዚህ በኋላ ጋኔን ዕውር ደንቆሮ ድዳ ያደረገውን ሰው ወደሱ አመጡ ።
ወፈወሶ እስከ ውእቱ ዕውር ወጽሙም ነበበ ወርእየ ወሰምዐ ።
ዕውረ ሥጋው በታምራት ዕውረ ነፍሱ በትምህርት እስኪያይ በሐመ ሥጋው በታምራት በሐመ ነፍሱ በትምህርት እስኪናገር ፤ ጽሙመ ሥጋ በታምራት እስኪሰማ ድረስ አዳነው

፳፫ ወተደሙ ኵሎሙ አሕዛብ ፤

፳፫ አሕዛብ ሁሉ አደነቁ ።
ወይቤሉ አኮኑ ዝንቱ ወልደ ዳዊት ።
ያላመኑት ። የጥቡዕ የዳዊት ልጅ አይደለምን ይህን ይህል ርኅራኄ ከማን አገኘው ብለው ። ያመኑት ግን የርኅሩኅ የዳዊት ልጅ አይደለምን ምነዋ ቢያደርግ አሉ ።

፳፬ ወፈሪሳውያንሰ ሰሚዖሙ ይቤሉ ዝንቱሰ ኢያወፅእ አጋንንተ ዘእንበለ በብዔል ዜቡል መልአከሙ ለአጋንንት ። ማቴ ፱ ፣ ፴፬ ማር ፡ ፫ ፣ ፳፪ ፡ ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፲፭ ።

፳፬ ፈሪሳውያን ግን ሰምተው ታምራት ይደረጋል ሰው ይሰበሰባል ወንጌል ትሰፋለች ኦሪት ትጠፋለች ብለው የንጉሥን ጭፍራ በንጉሥ ቀላጤ እንዲያስወጡት ካለቃቸው ከብዔል ዜቡል ተጨዋውቶ ያወጣቸዋል እንጂ ያለዚያ አያወጣቸውም አሉ ።

፳፭ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ሕሊናሆሙ ይቤሎሙ ኵላ መንግሥት እንተ ትትናፈቅ በበይናቲሃ ትማስን ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ።

፳፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነገራቸውን ዐውቆባቸው እርስ በርሷ የምትለያይ መንግሥት ሁሉ ትጠፋለች አላቸው ንጉሥ እንዝመት ሲል ሠራዊቱ አንዘምትም ቢሉ ።

ወኵላ ሀገር ።
እርስ በርሷም የምትለያይ ሀገር አትጸናም ፡ ትፈታለች ሹሙ አንገብር ሲል ሕዝቡ አንገብርም ቢሉ ። ወእመኒ ቤት እንተ ትትናፈቅ በበይናቲሃ ኢትቀውም እርስ በርሷም የምትለያይ ቤትም አትጸናም ትፈርሳለች ። ባለቤቱ ደጋ እንሁን ሲል ቤተሰቡ ቆላ እንሁን ቢሉ ።

፳፮ ወእመሰ ሰይጣን ያወፅእ ሰይጣነ ተናፈቀኬ በበናይቲሁ ፤ ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያወጣው ከሆነ እርስ በርሱ ተለያየ ።

፳፮ እፎ እንከ ትቀውም መንግሥቱ ።
መንግሥቱስ እንደምን ትጸናለች ፤ ሐተታ ምን መንግሥት አለው ቢሉ ዮሐንስ ወልደ ማሬት እንዳየው ፤ አባቱ መምለኬ ጣዖት ነበረ ለጣዖት ሊሰዋ ሲሄድ አስከትሎት ሄደ ሠውቶ እስኪወጣ ዕንቅልፍ መጣበት ተኛ በሕልሙ ዲያብሎስ በአምሳለ ንጉሥ ዘውዱን ደፍቶ ከዙፋኑ ሁኖ ኃያላኑን በቀኝ በግራ በፊት በኋላ አቁሞ ያየዋል ከዱሬ መጥቶ ንገሩልኝ ይላል ይነገሩለታል ይገባል ወዴት ነበርህ ይለዋል ከሀገር ፡ ምን አድርገህ መጣህ ይለዋል ባልና ሚስቱን ነገር ካለተ በኋላ አጣልቼ አለያይቼ መጣሁ ይለዋል በስንት ቀንህ ነው አለው ባ ፲፭ ቀኔ ነው አለው ። አስወጣው አለው ። ሌላው መጥቶ ንገሩልኝ አለ ይነግሩለታል ገባ በሉት ይላል ይገባል ወዴት ነበርህ አለው ከምድር ድምበር ፡ ምን አድርገህ መጣህ ይለዋል ወንድማማች አጣልቼ አጋድዬ መጣሁ ይለዋል በስንት ቀንህነው ፳ ቀኔ ነው አለው ይለዋል አስወጣው ይላል ይወጣል

ደግሞ መጥቶ ንገሩልኝ ይላል ይነግሩለታል ይገባል ወዴት ነበርህ ይለዋል ከባሕር ፡ ምን አድርገህ መጣህ ይለዋል ነፋስ አምጽቼ ማዕበል ሞገድ አስነሥቼ መርከቡን ገልብጬ ሰውን አስጥሜ መጣሁ ይለዋል ስንት ቀንህ ነው ፴ ቀኔ ነው አለ አስወጣው አለ ። ደግሞ ሌላው መጥቶ ንገሩልኝ ይላል ይነግሩለታል ግባ በሉት ይላል ይገባል ወዴት ነበርህ ይለዋል ከገዳም ምን አድርገህ መጣህ ይለዋል ፵ ዘመን የዘጋውን መነኩሴ አስቼ ዓለማዊ ሥራ አሠርቼው መጣሁ አለው በስንት ቀንህ አለው በዘመኑ ልክ ተዋግቼ አለው አንተንስ ሊያነግሡህ ይገባል ብሎ ከዙፋኑ ወርዶ ዘውዱን ደፍቶ ሲያነግሠው አየ ። ሲነቃ የመነኮሳት መከራቸው የጸና ክብራቸው እንጂ ቢበዛ ነው ብሎ አምኑዋል ተጠምቋል መንኵሷል ።

፳፯ ወእመሰ አነ በብዔል ዜቡል አወፅኦሙ ለአጋንንት ውሉድክሙ በምንት ያወፅእዎሙ ፤

፳፯ እኔ አጋንንትን በብዔል ዜቡል የማወጣቸው ከሆነ ልጆቻችሁ ሐዋርያት በማን ስም ያወጧቸዋል በኔ ስም አይደለምን ወበእንተዝ እሙንቱ ፈታሕተ ይከውኑክሙ ።
ስለዚህ ነገር ማለት እናንተ በብዔል ዜቡል ያወጻል ስላላችሁኝ ሐዋርያት በኔ ስም የሚያወጣቸው ስለሆነ እነሱ መፈራረጃ ይሆኑባችኋል ።

፳፰ ወእመሰ አነ በመንፈስ እግዚአብሔር አወፅኦሙ ለአጋንንት የጊኬ በጽሐት ላዕሌክሙ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፳፰ እናንተ አጋንንትን በብዔል ዜቡል ያወጣቸዋል የምትሉኝ ከሆነ እኔ ግን አጋንንትን በመንፈስ እግዚአብሔር የማወጣቸው ከሆነ ሥልጣነ እግዚአብሔር ልታጠፉችሁ ተቃጥታባችኋለች እንድም እናንተ በመንፈስ እግዚአብሔር ያወጣቸዋል ካላችሁኝ እኔም በመንፈስ እግዚአብሕር የማወጣቸው ከሆነ መንግሥተ እግዚአብሔር ልጅነት ልትሰጣችሁ ቀርባለች ።

፳፱ ወአልቦ ዘይክል መኑሂ በዊአ ቤተ ኃያል ወበርብሮ ንዋዮ ፤

፳፱ ካርበኛ ቤት ገብቶ ገንዘቡን መዝረፍ የሚቻለው የለም ።
አመ ኢተደመ ዓሚርቶ ለኃያል
አስቀድሞ እጁን ካላያዘው ወእምዝ ይበረብር ቤቶ
እጁን ከያዘ በኋላ ገንዘቡን ይወስዳል እንደዚህም ሁሉ ሰይጣንን በፎቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ነሥቼ ዋሰሁና አወጣዋለሁ እንጂ ያለዚያ አላወጣውም።
፴ ዘኢኮነ ምስሌየ ዕድውየ ውእቱ
፴ በቦታ በቅዳሴ ከኔ ጋራ አንድ ያይደለ ዲያብሎስ ባለጋራዬ ነው ፤
ወዘኢይትጋባእ ምስሌየ ይዘርወኒ ።
በቦታ በቅዳሴ ከኔ ጋራ አንድ ያይደለ ዲያብሎስ በምእመናን እንዳላድርባቸው ያደርገኛል ።
የምእመናንን ዝርወት አንድ አድርጎ ይዘርወኒ አለ። አንድም ዘኢኮነ ምስሌየ ፡ በሃይማኖት በጉባኤ ከኔ ጋራ አንድ ያይደለ ይሁዳ ባለጋራዬ ነው ። ወዘ ኢይትጋባእ ፡ በሃይማኖት በጉባኤ ከኔ ጋራ አንድ ያይደለ ይሁዳ ፡ በመእመናን ፡ አንድም በሱ እንዳ ላድርበት ያደርገኛል ።
፴፩ ወበእንተዝ እብለክሙ ኵሉ ኃጢአት ወጽርፈት ይትኃደግ ለሰብእ ። ማር ፫ ፡ ፳፰ ፡ ሉቃ ፡ ፲፪፡፲
፴፩ ስለዚህ ሰውን የሰደበ ሁሉ ኃጢአቱ ይሰረይለታል ብዬ እነግራችኋለሁ ።
ወዘሰ ጸረፈ ላዕለ መንፈስ ቅዱስ ኢይትኃደግ ሎቱ መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ግን ማለት ሕጹጽ ያለ ኃጢአቱ አይሰረይለትም ።
፴፪ ወዘሰ ነበበ ቃለ ላዕለ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ይትኃደግ ሎቱ ።
፴፪ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን ግን ፅሩቅ ብእሲ ያለ ይሰረይለታል ።

ወዘሰ ነበበ ላዕለ መንፈስ ቅዱስ ኢይትኃደግ ሎቱ መንፈስ ቅዱስን ሕጹጽ ያለ ግን ኃጢአቱ አይሰረይለትም ፡ ይህን ማለቱ ይገባዋል ብሎ አይደለም ለወልድ ምክንያት አለው ሥጋ ለብሷል ። ለመንፈስ ቅዱስ ግን ምክንያት የለውምና ከቲዘጋ ቤቱ ከተዳፈነ እሳቱ እንዲሉ እንድም አብ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ሳይመሰክርለት ዕሩቅ ብእሲ ያለ ኃጢአቱ ይሰረይለታል ።

አብ ዝንቱ ውእቱ ብሎ ከመሰከረ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከመሰከረለት በኋላ ግን ዕሩቅ ብእሲ ያለ አይሰረይለትም ። እንድም ሕዝባዊን የሰደበ ኃጢአቱ ይሰረይለታል ። ኤጲስ ቆጶሱን የሰደበ ግን ኃጢአቱ አይሰረይለትም ።

እንድም ሥጋዊ ተዘምዶን ያፈረሰ ኃጢአቱ ይሰረይለታል መንፈሳዊ ተዘምዶን ያፈረሰ ግን ኃጢአቱ አይሰረይለትም ኃጢአት ሥጋውያት ይሰረያ በጾም ወበጸሎት ፡ ኃጢአትሰ መንፈሳውያት ኢይሰረያ በጾም ወበጸሎት ዘእንበለ ዳዕሙ በምንኵስና እንዲል ፤ እንዲህ ማለት ንስሐ ከገባ አይሰረይለትም ማለት አይደለም ከቀኖና ቀኖናውን ከፍዳ ፍዳውን ማብለጥ ነው ።

ኢበዝ ዓለም ።
በዚህም ዓለም ሁኖ ።
ወኢበዘይመጽእ ዓለም ።
በሚመጣውም ዓለም ሁኖ አይሰረይለትም ። በወዲህስ ይሁን በወዲያማ ምን ንስሐ አለ አልቦቱ ለሰብእ ንስሐ እምድኅረ ሞት ይል የለም ቢሉ ፡ ኃጢአቱን ለቄሱ ነግሮት ቀኖና ተቀብሎ ጀምሮት ቢሞት ሳይጀምረውም ቢሞት መካነ ንስሐ አለ ከዚያ አድርሶ ይወጣልና እንዲህ አለ ። እንድም ወትጼሎ አበሳነ ምስለ ኵሉ ዘገበርነ እንዲል ያለማነውም ያጠፋነውም በፍትሐ እግዚአብሔር ይመረመራል ያለማነው በዝቶ ያጠፋነው ያነሰ እንደሆነ እንገባለን ያለማ ነው አንሶ ያጠፋነው የበዛ እንደ ሆነ ግን አንገባምና ።

፴፫ እመ አኮ ግበሩ ዕፀ ሠናየ ወፍሬሁኒ ሠናይ

፴፫ እመ አኮ ዋዌ ነው መልካም ዛፍ አድርጉ ፍሬውም መልካም ማለት የአብርሃም ልጆች ነን ባሉ የአብርሃምን ሥራ ሥሩ ። እንድም ተነሣሕያን ነን ባሉ እኔም ተራድቼ የተነሳሕያንን ሥራ ሳሠራችሁ ።

ወእመ አኮ ግበሩ ዕፀ እኩየ ወፍሬሁኒ እኩይ ።

ወይም ክፉ ዛፍ አድርጉ ፍሬውም ክፉ ማለት የሰይጣን ልጆች ነን ባሉ የሰይጣንን ሥራ ሥሩ እሱስ አያዛቸውም እንዳይተውት ያውቃልና ፤ እንድም ፡ በአፋቸው እንወድሃለን ይሉታል በልቡናቸው ይጸሉታል በአፋችሁም በልቡናችሁም ወደዱኝ ፤ ያለዚያ ግን በአፋችሁም በልቡናችሁም ጥሉኝ ፡ እንድም ሥራውን የአምላክ ሥራ ነው ይላሉ እሱን ዕሩቅ ብእሲ ይሉታል ሥራየን የአምላክ ሥራ ነው ባሉ እኔንም አምላክ ነው ባሉ ያለዚያ ግን እኔንም ዕሩቅ ብእሲ ባሉ ሥራዬንም የዕሩቅ ብእሲ ሥራ ነው ባሉ ። እንድም ታምራቱን ይወዳሉ ትምርቱን ይጸላሉ በአንተ ሠናይሰ ግብርከ ኢንቴግረከ ኣላ በበይነ ዕርፈትከ እንዲል ታምራቱንም ትምርቱንም ውደዱ ያለዚያ ግን ትምርቱንም ታምራቱንም ጽሉ ። እስመ እምፍሬሁ ይትዓወቅ ዕፀ ።
ዛፍ በፍሬው ይታወቃልና ።
በአንተ ጽልሁት ዘፈሪሳውያን

፴፬ ኦ ትውልደ ዓራዊተ ምድር በአይቴ ትክሉ ሠናየ ተናግሮ እንዘ እኩያን አንትሙ ።

፴፬ እናንት የእባብ ልጆች ክፉዎች ስትሆኑ መልካም መናገር እንደምን ይቻላችኋል በልቡናችሁ ዕሩቅ ብእሲ የምትሉ ስትሆኑ እኔን የባሕርይ አምላክ ማለት እንደምን ይቻላችኋል ።

እስመ እምተረፈ ልብ ይነብብ አፍ ፤
ልብ ያሰበውን አፍ ይናገራልና ።

፴፭ ኄር ብእሲ እምሠናይ መዝገበ ልቡ ያወፅእ ሠናይተ ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፵፭ ።

፴፭ በጐ ሰው በጐ ነገር ከሚያስብበት ልቡናው በጐ ነገርን አውጥቶ ይናገራል ።
ወእኩይሰ ብእሲ እምእኩይ መዝገበ ዓመጻሁ ያወፅእ ለእኪት ክፉ ሰው ግን ክፉ ነገር ከሚያስብበት ልቡናው ክፉ ነገርን አውጥቶ ይናገራል ።

፴፮ አንሰ እብለክሙ ኵሉ ሰብእ ዘይነብብ ንባበ ጽሩዓ ያገብኡ ሎቱ በእንቲአሁ ቃለ በዕለተ ደይን ።

፴፮ እኔ ግን ተርታ ነገርን በሚናገር ሰው ሁሉ በፍርድ ቀን ፍዳውን ያመጡበታል ብየ እነግራችኋለሁ ። ታሪክ እንዳንድ ባሕታዊ ከሚረዳበት ገዳም ወጥቶ በተባሕትዎ ይኖራል ከማኅበሩ አንዱ ሊጠይቀው ሄደ አነአገሌ እንደምን ሁነዋል ብሎ ጠየቀው የበቁ ሁነዋል አለው ። አንድ ሕሙየ ግብር ነበር እገሌሳ አለው እሱስ ከሁሉ በልጧል አለው አፍ ፡ እስካሁን የነገርኸኝ ሁሉ ሐሰት ነው ለልማዱ ጌታ በአምሳለ ንጉሥ ሲገኝለት እሱም የብርሃን ካባ ለብሶ በቀኝ ሲቆም የሚያየው ነው ። እንደወትሮ የብርሃን ካባ ለብሶ በቀኝ እቆማለሁ ብሎ ሲሄድ ምስለኔየ ወሬኛየ መንግሥት ተበሳልጨ መጣህ ንሳ ያዘው ሲል እሻላሁ ብሎ ሲሄድ ካባው ተገፎ ሲቀር አየ እንዲህ ብየ በተናገርሁት ፈጣሪየ ፈርዶብኝ ነውን ብሎ ንስሐ ቢገባ በሰባት ዓመቱ ጌታ እንደ ጥንቱ በአምሳለ ንጉሥ ሲገኝ እሱም የብርሃን ካባ ለብሶ በቀኝ ሲቆም አይቷል ።

፴፯ እስመ እምቃልከ ትጸድቅ

፴፯ ከንጋገርህ የተነሣ ትከብራለህና ወእምቃልከ ትትኴነን

ከንጋገርህ የተነሣ ይፈረድብሃልና ፤ ኢዮብ መ ጠንከ እምቃለ አፉከ ፤ ሰሎሞን ሕይወት ወሞት ውስተ እደ ልሳን ፤ ሲራክ ኃሳርከኒ ወክብርከ እምቃለ አፉከ ያሉትን ቃል ለውጦ አነበበው

በእንተ ትእምርተ ዮናስ ።

፴፰ ወእሜሃ መጽኡ ሰብአ እምጸሐፍት ወእምፈሪሳውያን ወይቤልዎ ሊቅ ንፈቅድ እምኔከ ትእምርተ ንርአይ ።

፴፰ ያን ጊዜ ከጸሐፍት ከፈሪሳውያን ወገን የሚሆኑ ሰዎች መጥተው መምር ምልክት ልታሳየን እንወዳለን አሉት ። ሐተታ ፤ እሉ ሰው ሁኖ በቋንቋቸው በዕብራይስጥ ቢያስተምራቸው እንደ ሙሴ ባሕር ከፍለህ ጠላት ገድለህ ደመና ጋርደህ መና አውርደህ እንደ ኢያሱ በረድ አዝንመህ ፀሐይ አቁመህ እንደጌዴዎን ፀምር ዘርግተህ ጠል አውርደህ እንደ ኤልያስ ሰማይ ለጕመህ እሳት አዝንመህ ልታሳየን እንወዳለን አሉት ።

፴፱ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ትውልድ ዕሉት ወዓማፂት ወዘማዊት ትእምርተ ተኀሥሥ ፡ ማቴ ፲፮ ፡ ፬ ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፩ ፡ ፳፪ ፡

፴፱ ሴሰኛ አሉተኛ ትውልድ ቤተ አይሁድ ምልክትን ትሻለች ። ቤተ አይሁድን ዘማ አላቸው ዘማ ነገሩ አንድ ሲሆን ዕለት ዕለት ወንድ ሲለወጥላት እንድትወድ ቤተ አይሁድም ዕለት ዕለት ትምህርት ቢለወጥላቸው ይወዳሉና ። ወትእምርትስ ኢተውሀባ ዘእንበለ ትእምርተ ዮናስ ነቢይ ፤ ምልክት ግን ዮናስ ካደረገው ምልክት በቀር ያልተደረገላት የቀረባት የማይደረግላት የማይቀርላት የለም ። ሁሉን ስትዘነጋው ይህን አትዘነጋው ምና ኋላ በመጨረሻ ተዘከርነ ዘይቤ ቅንቱ መስሐቲ አመ ሕያው ውእቱ አመ ማልስት ዕለት እትነሣእ አዝዝ እንከ ይዕቀቡ መቃብሪሁ ይላሉና ።

፵ እስመ በከመ ነበረ ዮናስ ውስተ አንበሪ ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ ከማሁ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ይንበር ውስተ ልበ ምድር ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ ። ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፩ ።

፵ ዮናስ በከርሠ አንበሪ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት እንደ ኖረ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስም ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ይኖር ዘንድ አለውና ።

፵፩ ሰብአ ነነዌ ይትነሥኡ አመ ዕለተ ደይን ምስለ ዛ ትውልድ ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፭ ።

፵፩ የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን በቤተ አይሁድ በጸላትነት ይነሣባታል ።

ወይትፋትሕዋ ።

ይከራከሯታል ።

ወያስተሐፍርዋ ።

ምላሽ ያሳጧታል ።

እስመ ነስሑ በስብከተ ዮናስ ፤

ዮናስ ቢያስተምር አምነዋልና ።

ወናሁ ዘየዐቢ እምዮናስ ሀሎ ዝየ ።

ከዮናስ የሚበልጥ እነሆ ከዚህ አለ ማለት ቤተ አይሁድ ግን እግዚእ ዮናስ ክርስቶስ ቢያስተምራቸው አናምንም ብለዋልና ።

ጌታ ዮናስን እለቱ ሠሉስ ዕለት ትትገፋዕ ነነዌ ሀገር ሀቢይ እያልህ አስተምር አለው አይሆንም አንተ መሐሪ ነህ እኔ እንዲህ ብየ አስተምሬ ብትምራቸው ነቢየ ሐሰት እባል የለም አለው ሁለተኛ ሂድ አላልሁምን አለው ዮናስ ማለት ርግብ የዋህ ማለት ነውና ይህ ሁሉ የሚዘበዝበኝ ከሬቱ ቢያገኝኝ አይደለም ብሎ ውቱኃቢእ እምገጸ እግዚአብሔር ወሖረ ተርሴስ ይላል ተርሴስ ወደሚባል ሀገር ሲሄድ ኢዮጴ ከሚባል ባሕር ደረሰ ወረከበ ሐመረ ዘይነግድ ብሔረ ተርሴስ ይላል ፤ በሀገራቸው ከየብሱ ባሕሩ ይበዛልና ነጋድያን በመርከብ ተጭነው ወደ ተርሴስ ሲሄዱ አገኘ ወተአሰበ ሐመረ በንዋይ ይላል ገዝቶ ባንድነት ተጭኖ ሄደ ምንት ተግባርከ ወአይ ብሔርከ ወአይ ሕዝብከ አሉት አይ ብሔርከ ባሉት አይመልስላቸውም አይ ሕዝብከ ባሉት ዕብራዊ ነኝ ። ወምንት ተግባርከ ባሉት የማመልከው ሰማይን ምድርን የብስን ባሕርን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው አላቸው ከጥልቅ ባሕር ሲደርሱ ነፋስ መጣ ማዕበል ሞገድ ተነሣ መርከባቸው ሊሰጥም ሆነ ወገደፉ ማህሎሙ ይላል ፤ ገንዘባቸውን እያወጡ ይጥሉ ጀመር እንደ ማሟረት ፤ ወንሕረ ዮናስ ውስተ ከርሠ ሐመር ይላል ሊቀ ሐመር ከሚተኛበት ገብቶ ተኝቷል እንዲሄዶ ተንሥኡ ወጸውኡ ስመ አምላክከ አለው እግዚአብሔርን አመልካለሁ ብሏቸው ነበርና ነገሩን አይቶ ይህ የመጣ በኔ ምክንያት ነው እኔን ካልጣላችሁኝ ጸጥ አይልላችሁም አላቸው እባቸውም ሰውስ ብንጥል እዳ ይሆንብናል ዕጣ እንጣጣል ብለው ዕጣ ቢያወጡ ወወረደ ዕፃ ላእለ ዮናስ እንዲል በዮናስ ዕጣ ወጣበት ወረደ ማለቱ ግን ከራሳቸው አድርገው ያወጡታልና ፈቃድህስ ከሆነ ዕዳ አይሆንብንም ብለው አውጥተው ጣሉት የታዘዘ አንበሪ ተቀብሎ ዋጠው ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት አሳድሮ በአንጻረ ነነዌ አውጥቶ ጣለው ከዚህ በኋላ ወሰበከ ምሀዋረ አሐቲ ዕለት ይላል ያንድ ቀን መንገድ ሲቀር ያኑ አስተማረ ።

ያገሩ ንጉሥም ይኸን ነገር በሰማ ጊዜ ከዙፋኑ ወርዶ ማቅ ለብሶ አመድ ነስንሶ ንስሐ ገባ የወንድ ሙሽራ ከሚጉላው የሴት ሙሽራ ከመጋረ

፳፫ ይወጡ ኢይትረአዩ ሰብእ ወእንስሳ ለምኙም እንስሳትም ከዕንጨት ከሣር ከውኃ አይዙሙሩ ብሎ [illegible] ነገረ ይጠፋልኛል ብሎ በጾም የሚያጠፋለት ሆኑ እኔ አስቀድሜ የፈራሁት ይኸን አልነበረምን ብሎ ሐሰበ ፤ ዮናስ የሚል ድምፅ አሰማው ሊያድር ግለኝ ነው ብሎ ከከተማው ዳር ወንበረ ላይ ጎጆ ቁቁ ቀየተ ጸለለ ጎጆ ወቢቶ ተቀመጠ ዕንቅልፍ [illegible] ተኛቶ ኢያ ሁለተኛ ቢንያ ቅል በቅል ነጸውን ለልብዕለት አገኘ ደስ ብሎት ተኛ የታዘዘ ትል ቀርጦ ጣለው ጸሐዮች ቀዐይ ተሰማው ቢንያ ደርቃ አገኘት እዘን ጠየቁት ትቴክዝ ታዝናለህን አለው አዎን በልቤ አዝኛለሁ ሳልተክልሁት ወኃ ላላጠጣሁት ታዝናለህ ።

እንሰኑ ኢይምህካ ለነነዌ ሀገር ዘሀለወ በውስቴታ ፈድፋደ ዘይበዝኁ እም ፲፻ ወ፪፻ እልፍ እለ ኢያአምሩ የማናቸውን ወፀጋሞሙ እኔስ ግራና ቀኝ [illegible] ለሚወረዉሩ ፲፪ እልፍ የሚበዙ ኃያላት ልቡባት ለነነዌ እኔ አላዝንላቸውምን ፤

እንድም ግራና ቀኝ ያለዩ ከሥራ ሁለት እልፍ የሚበዙ ሕፃናት ላሉባት ለነነዌ እኔ አላዝላትምን አለው እሱም ነቢየ ሐሰት እንዳይባል እሳቱ እንደ ደመና [illegible] የታላላቁ ዛፍ ቅጠል እስከ [illegible] ደርሆ [illegible] እንዳይቀር ተመልሶላቸዋል [illegible] ቀን ወበልዓ [illegible] [illegible] ታሪኩ [illegible] ዓባይ [illegible] ንጉሥ ሰናከሬም [illegible] ሰናከሬምን ይመልጻል፤ ወሶበ ለምኡ [illegible] ሀገር ዓባይ ትፈሥሐ ቂሮስ ወእኽዋ [illegible] ሶንኬብ ሰናክሬም ነበር ስዱው እስ [illegible] ። ይህም ሊታወቅ ጦቢት ሲሞት ጦብያ ልጁን ይህች ሀገር ጠፊ ናት ዮናስ የተናገረው [illegible] ሜዶን ሂደህ ኑር ገንዘቦችንን ከነገለል እምጣ ብሎት ሞቷል ።

ዮናስ ነነዌ ወርዶ ማስተማሩ ስለምን ቢሉ አብነት ለመሆኑ ፤ ሐዋርያት ወንጌልን ሊያስተምሩ በሄዱ ጊዜ እኒህ ለምን ይመጣሉ ቀድሞ ነቢያት መጥተው እያስተምሩንም ነበር በምን ነገር ነው እንዳይሉ ልማድ እንጂ ነው ቀድሞም ነቢያት ያስተምሩን ነበር ብለው እንዲቀበሏቸው ። ፫ መዓልት ፫ ሌሊት መሆኑ ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ።

ትንቢት በስኑይ ዕለት ይቀሥፈነ ወበሠሉስ መዋዕል ያነሥአነ ወየሐይወነ ። ወአመ ሣልስት ዕለት ተንሥአ ፤ ወአመ ሣልስት ዕለት ሦጣ ለነፍሱ ውስተ ሥጋሁ ተብሎ ተነግሯል ።

ምሳሌም ከዚህ እስከ ብሩህ ሰማይ መልቶ የነበረውን [illegible] ከሦስት ከፍሎ አንዱን እጅ ውቅያኖስን ለያስተጋብእ ማይ ውስተ ምዕላሂሁ ብሎ በዙሪያው [illegible] አንዱን እጅ ሐኖስን ከላይ ሰቅሎታል አንዱን እጅ ለየብሱን ጠፈር ብሎ ባለው አጸንቶታል ውኃው የመቃብር ምድር የጌታ ምሳሌ እንድም አዳም በፈታሒነቱ አንጻር መሐረነቱ አንዳለ ዐውቆ በገነት ድለው እንደፈረደብን ንስሐ ብገባ እንጂ ይቅር ይለናል ብሎ እለካንነታቸው የሚያመልቅ ባሕር ገቡ ። እንቺም ከዚያ ግቢ እኔም ከዚያ እገባለሁ ብሎ አርባ ቀን ሳይሆን አንወጣም አሉ ። ሠላሳ አምስት ቀን ሲሆን ዲያብሎስ መጥቶ ምሬሃለሁ ውጣ ብሎሃል ሔዋን አርባ ቀን ሳይሆንኝ እልወጣም ብዬ ነው የገባሁ አይሆንም አለው ። ቀድሞ አትብላ ያለውን ዕፀ በለስ በልተሀ ከዚህ ሁሉ ደረስህ ደግሞ ዛሬ ምሬሃለሁ ውጣ ብሎሃል ብልህ እልወጣም አልክ ሳዘዘኝ እንግርልሃለሁ ብሎ የቁቆጣ መስሎ ወደ ሔዋን ሂደ ።

እስመ ይእቲ ገራህተ ሐምሉ ይላታል የበሰላው ናትና ቢመክሩት አይሰማ ምሬሃለሁ ውጣ ብሎሃል ብለው አይሆንም እል አሳት ሂዱ ምሬያችኋለሁ ሲለንማ እንውጣ እንጂ አለችው ተያይዘው ወጡ ተቂት እልፍ አድርጎ እኔ ማነኝ አላወቃችሁኝምን አላቸው አላወቅንህም አሉት ። ዕፀ በለስን ብሉ ብየ ከገነት ያወጣኋችሁ እኔ አይደለሁም ብሎ ተጥቅጦ ጥሏቸው ሄደ ። መልአክ መጥቶ በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እም ወለተ ወለትከ ብሎሃል ብሎ ተስፋውን ነግሮ ከገነት አንጻር በደብር ቅዱስ አኖራቸው ። ያን እያዩ እንዲያዝኑ ከዚህ ኑሩ አልከን ምግባችንስ አሉት ። ሳዘዘኝ እነግራለሁ ብሎ ገነት ገብቶ ለአእዋፍ ጌታችሁ አዳም ከዚያው ነው ምግቡን ውሰዱለት አላቸው ፤ ባንድ ሰዓት አሥራ ሁለት ዋሻ መልተውለታል ። ያንዱ ዋሻ ስፋት መጠኑ ምንዳፊ ሐጽ ። ይለዋል ሲሄዱ ወትሮ የሚያውቃቸው ናቸውና በድምጻቸው ተመሥጦ ተከተላቸው እኒያ ዋዩን እየበረሩ እሱ ታቹን እየሮጠ ተከታትለው ከእግረ ገነት ደረሱ ። የገነት ቅጽሩ እሳት ነው እኒያ ላዩን እየበረሩ ገቡ ፤ እሱ ጸጋው ተነሥቶታልና ተከልክሎ ቀረ ። ይህ ቢሔት ወዴት ይሄዳል ብሎ ቤት ያህል ደንጊያ ጫነበት ወተደብተረት ይእቲ እብን ላዕለ አዳም እንዲል ሦስት ቀን እንደ ድንጊያ ሁናለት በንብቷል ከዚህ በኋላ መላእክ አንስቶለት ተመልሷል። ደንጊያ የመቃብር አዳም የጌታ ምሳሌ እንድም አብርሃም ይስሐቅን በሕሊናው በሰዋው በሦስት ቀን ተነሥቷል ።

ሕሊና አብርሃም የመቃብር ይስሐቅ የጌታ ምሳሌ፤ እንድም የናስ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ አንበሪ ኑሯል ፤ የናስ የጌታ ከርሠ አንበሪ የመቃብር ምሳሌ ። ትንቢቱን ዐውቆ አናግሯል ምሳ

ሌውንም እንጂ ባመቀ አስመዐዷል ምሥጢሩ እንደ ምን ነው ቢሉ ለአዳም ለሔዋን ለሕፃናቱ ለሥጋ ለነፍሲ ለደመ ነፍስ እንደ ካሥለማጠየቅ ፤ አንድም ፫ቱ እድዋኒሁ ለሰብእ እንዲል ኃጢአትን ምክንፍዳን እንዳጠፋ ለማጠየቅ ። አንድም በዕውነትም እንደሞተ ለማጠየቅ ፈላስፎች ነፍሱ ከሥጋው ከይለይ ያም ከልቡ ወድቆ እስትንፋሱን ይከለክለዋል ብለው ከሞተበት ሰዓት ጀምረው እስከ ቀተዘት ሰዓት ድረስ አቆይተው ነው የሚቀብሩ የሚድንም አለ የሚሞትም አለ ፈዋና ተነሥቶ ቢሆን ሕልሞተም በሉ ነበርና በውኑት እንደሞተ ለማጠየቅ ያመስ ቢሆን ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት ወዴት ይገኛል ቢሉ መዓልተ ዓርብ ሌሊት ዓርብን ስቦ ሌሊተ እሑድ መዓልተ እሑድን ስቦ አንድም ከርሠ ሐዋርያቱን መቃብር ብሎ አንድም ዓርብ ከነግሀ እስከ ቀትር ብርሃን ከቀትር እስከ ሰዓት ጨለማ ሁኑዋል ፡ በሠርክ ብርሃን ሁኑዋል ።

ወፍና ሠርክ ይበርህ ብርሃን እንዲል ይህ ሁለት መዓልት አንድ ሌሊት የቅዳሜ ሌሊትና መዓልቱ የእሑድ ሌሊት ይህ ነው ።

፵፪ ንግሥተ ዓዜብ ትትነሣእ ለመ ዕለተ ደይን ምስለ ዛ ትውልድ ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፲፩ ፡ ፪ ፡ ሕጹ ፡ ፱ ፡ ፩።

፵፪ ንግሥተ ዓዜብ በፍርድ ቀን በቤተ አይሁድ ትነሣባታለች ወትትፋታሕ ።
ትከራከራታለች ።
ወታስተሐፍራ ።
ምላሽ ታሳጣታለች ።

እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን ።

የሰሎሞንን ጥበብ ልትሰማ ከጽንፈ ምድር መጥታለችና ወንጌላዊ በወዲያ ሁና ይጽፋልና የኛን አገር ጽንፈ ምድር አለው ።
ወናሁ ዘየዓቢ እምሰሎሞን ሀሎ ዝየ ።
ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ ማለት ቤተ አይሁድ ግን እግዚአ ሰሎሞን ክርስቶስ ቢያስተምራቸው አናምንም ብለዋልና ።

ታሪክ የሰሎሞንን ጥበብ እያመጣ የሚነግራት ታምሪን የሚባል ነጋዴ ወዳጅ ነበራት ሂጂ ልረዳው ብላ መቶ ሃያ መክሊት ወርቅ ተንከራ በኢትዮጵያ ይለዋል ሉል በወዲያ የማይገኝ በኛ አገር የሚገኝ ዝባድ ገጸ በረከት ይዛ ሄደች ስትሄድም እያዘራች ሄዳለች ስትመለስ ስንቅ ሊሆናት አገር እንዳትዘርፍ ከእግሯ እንደ ምዳቋ ቀንድም እንደ አህያ ሰኰናም ቢሉ ነበረበት ኪደባባይ ስትደርስ ብላቴና አይቶ ገብቶ ንጉሥ በዘመንህ የማይመጣ የለም እንዲህ ያለች ሴት መጥታለች አለው ግቢ በላት አለው ስትገባ ከደጁ ወድቆ የሚኖር ግንድ ነበር ብትራመደው ወልቆ ወደቀላት አሱዋን አይቶ በዓይን መዓት አየው ።

ንጉሥ ባላይ አልነገርሁህም ጠይቀህ ቅጣኝ አለው ፤ ቢጠይቃት እውነቱ ነው ነበረብኝ ነገር ግን ከደጅህ የወደቀ ገበሬ ታምሪት ዕፀ አለ አቆ ፈወሰኝ እንጂ አለችው ነቢ እንደ ብር እሉ አንድ ብር ሸበውበታል ከሱ በኋላ ሃያ ሰምንት ነገሥታት ነግሠዋል ሃያ ሰምንት ብር ይሸቡበታል ፡ ወርቁን ለይሁዳ ሰጥተው በዕንጨቱ ጌታን ሰቅለውታል።

ሐሪፃ ወይን ዘእምጋሎሃን ይትዓዘም ወበጎል ጎታ ይተክል ከነ መድኃኒቴየ አሽዲል ። ብዙ አንቆትልሽ ጠይቀዋለች ፡ ወአልቦ ዘኢፈከረ ላቲ ወዘ ተሰወረ እምኔሁ ፡ ተሰውሮት የቀረ ያልተረጐመላት የለም ።

አሱም ከዚየ ድረስ መጥታ ሥርዓተ መንግሥት እናሳያት እንጂ ብሎ እሱዋ ሁሉን ከምታይበት አፈ ከማትታይበት ቦታ አኑሮ ሥርዓተ መንግሥት አሳያት ። ከዚህ በኋላ በጄ በይኝ አላት የሀገራችን መንግሥት በድንግልና ነው አይሆንም አለችው እንኪያስ አንችም የኔን ገንዘብ አልነካም ብለሽ ማይ አላት ማለች ።

የሚያጸግ ምግብ ሰጥቶ የምትጠጣውን ነሣት ሰሎሞን ቢተኛ እንደ አንበሳ ዓይኑን ያፈጣል ቢነቃ ይጨፍናል ተኝቶ ሳለ ያየኛል ብላ ዝም ብላለች ነቅቶ ሳለ አሁንስ አያየኝም ተኝቷል ብላ በጥበብ ያገባው ውኃ አለ ቀድታ ልትጠጣ መንቀል ይዛ ቀረበች እጅዋን ያዛት አንች ከኔ ገንዘብ ላትነኪ እኔም ያንቺን ገንዘብ ላልነካ መሐላ አልነበረንም አላት ይህማ ውኃ አይደለም አለችው ከውኃ የበለጠ አለ አላት ያሁኑን ተወኝ ፈቃድህን ትፈጽማለህ አለችው ተገናኙ ምኒልክ ተፀነሰ ወጥታ ስትሄድ ዓምደ ብርሃን ተከትሏት ቢሄድ አይቶ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ሄደች ብሎ ትንቢት ተናግሯል ።

ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው ፡ ንግሥተ ዓዜብ የዚህ ዓለም ሰሎሞን የጌታ ፻፳ መክሊተ ወርቅ የመቶ ሃያ ቤተሰብ መቶ ሃያ መክሊተ ወርቅ የተገኘ ከሱዋ ነው መቶ ሃያ ቤተሰብ የተገኙ ከዚህ ዓለም ነውና ፤ ዕንቁ የሃይማኖት ዝባድ የተዋልጦተ ገድል ምሳሌ ፤

በእንተ መናፍስት ርኩሳን ።

፵፫ ወእምከመ ወፅአ መንፈስ ርኩስ እምሰብእ የዓውድ በድወ ኀበ አልቦ ማይ ፡ ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬ ።

፵፫ መንፈስ ርኩስ ሰይጣን በጸበል በጸሎት ከሰው ከተለየ በኋላ ወደሌለበት ወደ የብስ ይሄዳል ፡ እሱስ ወኃ ወዳለበት ይሄዳል ገላቸውን ቢታጠቡ ልብሳቸውን ቢያጥቡ አድርባቸዋለሁ ብሎ መንፈስ ቅዱስ ወደ የብስ የሚወስደው ስለሆነ እንዲህ አለ እንጂ አንድም ወደ ኢጥሙቃን ይሄዳል እሱስ የሚሄድ ወደ ጥሙቃን ነው መንፈስ ቅዱስ ግን

ሙ ሊፈትኑትን የሚመስለው ስለሆነ እንዲህ አለ እንጂ ።

እንዘ የኃሥሥ ዕረፍተ ።
ዕረፍትን ማለት ማደሪያ ሲሻ ወየኃጥእ ። አያገኝም ሁሉ ገንዘቡ ሆኖ ፤

፵፬ ወእምዝ ይብል እገብእ እንከሰ ውስተ ቤትየ እምኀበ ወፃእኩ እምኔሁ ፤

፵፬ ከዚህ በኋላ እስኪ ቀድሞ ወደነበርሁበት ወደ ቀደመ ቦታዬ ልመለስ ብሎ ያስባል ፤ እንደ ባለ ርስት ባጠገብ ባጠገብ ሁኖ መጎብኘቱን እየ ተመለከተ ወመጺአ ይረክቦ ዕሩቀ ወኩሱቱረ ወምሩገ። በመጣም ጊዜ ባዶውን ያገኘዋል ማለት አሉቱን አበሉን ትቶ ያገኘዋል ።

፵፭ ወእምዝ የሐውር ወያመጽእ ምስሌሁ ካልኣነ ሰብዓተ መናፍስተ እለ የአክዩ እምኔሁ ። ፪ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳ ።

፵፭ ከዚህ በኋላ እሰይ ብሎ ሄዶ በክፋት ከሱ የሚጸኑ ሰባት አጋንንት ይዞ ይመጣል ።
ወበዊኦሙ የኃድሩ ውስቴቱ ።
መጥተው ያድሩበታል ።
ወይከውን ደኃሪቱ ለውእቱ ብእሲ ዘየዓኪ እምቀዳሚቱ ።
የዚያ ሰው ከቀደመ ሥራው የኋላ ሥራው የከፋ ይሆናል ። ሁሉም እየረከሱ ሥራ ያሠሩታልና ።

[illegible] ይኸውና ለዛሬ ትውልድ በቤተ አይሁድ እንዲህ ይደረግባታል ፤ አንድም ወእምከመ ወፅአ ፡ እሥራኤል በግብጽ ሳሉ እምልኮተ እግዚአብሔርን ይዘው ቢገኙ ተለይቷቸው ከሄደ በኋላ የንውድ በድወ ሃይማኖት ምግባር ወደሌላቸው ወደ አሕዛብ ይሄዳል ፤ እንዘ የኃሥሥ ፤ ማደሪያ ሲሻ ፤ ወየኃጥእ ፤ አያገኝም ሁሉ ገንዘቡ ሁኖ ሳለ ያጣል ። ወእምዝ ይብል ፤ ከዚህ በኋላ እስኪ ከቀድሞው ቦታዬ ልመለስ ብሎ ያስባል ።

ወመጺአ ፤ እስኪ ቀድሞ ወደነበርሁበት ልመለስ ብሎ በተመለሰ ጊዜ ብፁዕ ዘይበልዕ እምፍርፋሪ ማዕዱ ለፈርዖን ወዘይሰቲ እማየ አይጋቲሃ ለግብጽ ሲሉ እንደ ተገኙ ፤ ቤተ አይሁድም በመንፈስ እግዚአብሔር ያወፅአሙ ለአጋንንት ሲሉ ቢገኙ ተለይቷቸው ሄዶ ማደሪያ ሲሻ ሁሉ ገንዘቡ ሆኖ ያጣል ፤ እስኪ ወደ ቀደመ ቦታዬ ልመለስ ብሎ በተመለሰ ጊዜ በብዔል ዜቡል ያወፅአሙ ለአጋንንት ሲሉ መገኘታቸውን መናገር ነው ።
ወእምዝ ያመጽእ ፯ተ ካልዓነ እሥራኤል ብፁዕ ዘይበልዕ እምፍርፋሪ ማዕዱ ሲሉ ቢገኙ እሰይ ብሎ በክፋት ከሱ የጸኑ ሰባት አጋንንት ይዞ መጥቶ ባደረባቸው ጊዜ አሮን አሮን ግበር ለነ አማልክተ ዘየሐውሩ ቅድሜነ ወዘይጸብኡ ፀረነ እስመ ዝኩ ሙሴ ዘአውፅአነ እምድረ ግብጽ ኢነአምር ከመ ምንተ ኮነ ብለው በኮሬብ ስብኮ ላህም እንዲቆሙ ቤተ አይሁድም በብዔል ዜቡል ያወፅአሙ ለአጋንንት ሲሉ ቢገኙ በክፋት ከሱ የሚጸኑ ሰባት አጋንንት ይዞ መጥቶ አደረባቸው ባደረባቸውም ጊዜ ስቅሎ ማለታቸውን መናገር ነው ። ከማሁ ይከውና በቤተ አይሁድ አሁን እንደተናገርሁት ይደረግባታል ። አንድም ወእምከመ ወፅአ መንፈስ ርኩስ መንፈስ ርኩስ ሰይጣን በአንብዕ በትሕርምት ከሰው ከተለየ በኋላ ፤ የንውድ በድወ ኀበ አልቦ ማይ ዕንቡ አልቆ ደም ፤ ደሙ አልቆ አዝን አዝት አልቆ ይቡስ ከሆነው ባሕታዊ ይደርሳል ሳትሕርምቱ ከንቅጠሉ ከተወው ባሕታዊ ይደርሳል ። እንዘ የኃሥሥ ማደሪያ ሲሻ ወየኃጥእ አያገኝም አሁን የተመቸ እንደ እሳት ያቃጥለዋል ፤ ወእምዝ ይብል ከዚህ በኋላ ወደ ቀደመ ቦታዬ ልመለስ ብሎ ያስባል ። ወመጺአ ይረክቦ ዕሩቀ ፤ በተመለሰም ጊዜ ዕሩቀ ከትሩፋት ባዶ ሆኖ ወኩሱቱረ ወደ ኃጢአት ተጨልጦ ሄዶ ወምሩገ ፤ በኃጢአት ተለስኖ ያገኘዋል ወእምዝ ይብል ከዚህ በኋላ እሰይ ብሎ ሄዶ በክፋት ከሱ የጸኑ ፯ አጋንንት ይዞ መጥቶ ያድርበታል ። ወየዓኪ ደኃሪቱ ፤ የዚያ ሰው ከቀደመ ሥራው የኋላ ሥራው የጸና ይሆናል አለ ከበቃ በኋላ ዓለማዊ ሥራ ያሠሩታልና ።

፵፮ ወእንዘ ይነግሮሙ ዘንተ ለሕዝብ ናሁ እሙ ወአኃዊሁ ይቀውሙ አፍአ እንዘ ይፈቅዱ ይትናገርዎ ።

፵፮ ማር ፡ ፫ ፥ ፴፩ ሉቃ ፡ ፰ ፡ ፲፱ ለሕዝቡ ይህን ሲነግራቸው እናቱ እመቤታችን ወንድሞቹ ደቂቀ ዮሴፍ ሊገናኙት ወደው ከደጅ ቆመው ነበር ። ሐተታ እንዲያው አይደለም አንስ አብለከሙ አንስ አብለከሙ እያለ ሲያስተምር ልቡን ሻ ብሎት ሊሞት ነው የሚመክረው ዘመድ ያለውም ሲሉ ሰምተው ነው ።

፵፯ ወመጽአ አሐዱ እምአርዳኢሁ ወይቤሎ ናሁ እምከ ወአኃዊከ አፍአ ይቀውሙ ወየኃሥሡ ይትናገሩከ ።

፵፯ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ መጥቶ እነሆ ወንድሞችህና እናትህ ሊገናኙህ መጥተው ከደጅ ቆመዋል አለው ። ሐተታ እንዲህ ያለው ማነው ቢሉ ትምህርት ሊፈታ የሚወድ ሌላን አስያው ይሁዳ ነው እንጂ ፤

፵፰ ወአውሥአ ወይቤሎ ለዘነገሮ መኑ ይእቲ እምየ ።

፵፰ ለነገረው እናቴ ማናት ፤ ወእለ መኑ እሙንቱ አኃውየ ። ወንድሞቼስ እለ ማናቸው ብሎ መለሰለት ። ሐተታ መኑ ይእቲ እምየ ማለቱ እቢን መንቀፉ ነው ቢሉ አዎን በጊዜ ግብሮ ትምህርት የሚገኙበትን ሰዓት ጠይቆ መምጣት ይገባልና ፤

እሱዋንስ አይደሉቅፋትም ይህም ሊታወቅ ይእቲ ተግባ እምሱራፌል በንጽሕ ይላቃል ብሎ ከአክብሮተ አብ ወእምአክብሮቱ እግዚአብሔር እንዲበልጥ ለማ ጠየቁ ፤ እንድም ከጉባኤ መካከል መነሣት ይገባል ብለው አብነት እንዳያደርጉበት ።

፵፱ ወአመረ እዴሁ ኀበ አርዳኢሁ ።

፵፱ እጁን ወደ ደቀ መዛሙርቱ አመለከተ እጅ ሲነገር ያግዛልና ።
ወይቤሎሙ ናሁ እምየ ወአኃውየ ።
እናቴም ወንድሞቼም እነሆ በጉባዔ ያሉ ሕዝብ ናቸው አላቸው ፤

፶ እስመ ኵሉ ዘይገብር ፈቃዶ ለአቡየ ዘበሰማያት ውእቱ እኁየ ወእኅትየ ወእምየኒ ውእቱ ።

፶ የሰማይ አባቴን ፈቃድ የሚፈጽም ሁሉ ወንድሜም እኅቴም እናቴም እሱ ነውና ።

ምዕራፍ ፲፫ ።

፩ ወበይእቲ ዕለት ወፂአ እግዚእ ኢየሱስ እምቤት ነበረ መንገለ ሐይቀ ባሕር ።

፩ በዚያች ቀን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤት ወጥቶ ከወደቡ ተቀመጠ ።

፪ ወተጋብአ ኀቤሁ ሰብእ ብዙኃን እስከ ሶበ የዐርግ ውስተ ሐመር ወይነብር ማር ፡ ፬ ፡ ፩ ።

፪ ከመርከብ ወጥቶ እስኪቀመጥ ድረስ ብዙ ሰዎች ወደሱ ተሰበሰቡ ። ሐተታ ሰው ሲበዛ ከመርከብ ከተራራ ሆኖ ማስተማር ልማድ ነው ። መምህር ከፍ ካለ ቦታ ሰማዕያን ዝቅ ካለ ቦታ ሲሆኑ ትምህርት ለሰማዕያን ይረዳልና ። ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ እንዲል ።
ወኵሉ ሰብእ ውስተ ሐይቅ ይቀውሙ ።
ሕዝቡ ሁሉ ከወደቡ ተቀምጠው ነበር ወትቀውም ንግሥት በየማንከ እንዲል ፤ ባሕር የመለኮት ፤ ሐመር የትስብእት ምሳሌ ፤ መለኮቱን ትስብእቱን ከማመን በአፍአ እንደ ነበሩ ለማጠየቅ ውስተ ሐይቅ ይቀውሙ አለ ። እንድም ባሕር የትስብእት ሐመር የመለኮት ፤ መለኮቱን ትስብእቱን ከማመን በአፍአ እንደነበሩ ለማጠየቅ ውስተ ሐይቅ ይቀውሙ አለ እንድም ባሕር የጥምቀት ሐመር የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ከጥምቀት ከቤተ ክርስቲያን አፍአ እንደ ነበሩ ለማጠየቅ ውስተ ሐይቅ ይቀውሙ አለ ።

፫ ወነገሮሙ ብዙኃ በምሳሌ እንዘ ይብል ።

፫ ሉቃ ፰፥ ፭ እንዲህ ብሎ በምሳሌ ብዙ ነገራቸው ። እንድም ብዙኃ ምሳሌ ብዙ ምሳሌ ነገራቸው እንድም ወመሰለ ሎሙ ብዙኃ ምሳሌ ብዙ ምሳሌ መሰለላቸው ሐተታ ምሳሌውም በሆነ ነው እንጂ ባልሆነ ምሳሌ አይደለም ለገበሬ በዘር ለሴት በርሾ ለነጋዴ በዕንቍ ለዓሣ ወጋሪ በዘረ መትራን መስሎ አስተምሯል ። በምሳሌ ማስተማሩ ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ትንቢት እክሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር እምሳለ ዘእምትካት ተብሎ ተነግሯል ፤ ምሳሌም ቀድሞ አባቶቹ ነቢያት በምሳሌ እንበለ ምሳሌ አስተምረዋል እሱም በምሳሌ ይኸን እንበለ ምሳሌ ብፁዓንን አስተምሯልና ትንቢቱን ፀውቶ እናገሯል ምሳሌ ውንም እንጂ ባወቀ ኢሰሚዕዎ ምሥጢሩ እንደ ምንው ቢሉ ላዋቂ ለመግለጽ ካላዋቂ ለመሠወር ። እንድም ደቀ መዝሙር ሁል ጊዜ ተርታ ነገር ቢኑ ግሩት አይነቃምና ለማንቃት ።
ናሁ ወፅአ ዘራኢ ከመ ይዝራዕ ።
ገበሬ ሊዘራ ወጣ ዘሩም የተበጠረ የተንጠረጠረ ነው

፬ ወእንዘ ይዘርዕ ቦ ዘወድቀ ውስተ ፍኖት ።

፬ ጨብጦ ሲዘራ ከመንገድ የወደቀ ዘር አለ ።
ወመጽኡ አእዋፈ ሰማይ ወበልዕዎ ።
አዕዋፍ መጥተው የለቀሙት ።

፭ ወቦ ዘወድቀ ዲበ ኰኵሕ ኀበ አልቦ መሬት ብዙኀ ወውእቱ ጊዜ ሠረፀ ።

፭ ብዙ መሬት ከሌለው ከጭንጫ ላይ የወደቀ ፈጥኖ የበቀለ አለ ፀ ።
እስመ አልቦ ዕመቅ ለመሬቱ ።
ለመሬቱ ጥልቅነት የለውምና ፤

፮ ወሶበ ሠረቀ ፀሐይ መጽለወ ወየብሰ ፤

፮ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ጠውልጎ ደረቀ ።
እስመ አልቦ ዕመቅ ለመሬቱ
ለመሬቱ ጥልቅነት የለውምና ፤

፯ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ሦክ ።

፯ ከእሾህ መካከል የወደቀ ዘር አለ ።
ወበቍሉ ሦክ ጠበቆ ወሐነቆ ።
በበቀለ ጊዜ እንዳያድግ እሾህ አንቆ አስቀረው ።

፰ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ሠናይ ።

፰ ከበጎ ምድር የወደቀ ዘር አለ ።
ወወፅአ ፍሬ ።
ፍሬ ያቀረጸ
ቦ ፻ ።
መቶ ቅንጣት ።
ወቦ ፷ ።
ስሳ ቅንጣት ።
ወቦ ፴ ።
፴ ቅንጣት ያቀረጸ አለ ። እንድም ናሁ ወፅአ ብለህ መልስ ጌታ ሲያስተምር በው ሆነ ፀአተ ይሰሚ ሥጋዌሁ እንዲል ከዚህ ፀአተ አለ ሐዋርያው በአተ ይለዋል ፤ ወእንዘ ይዘርዕ ፤ ሰው ሁኖ ሲያስተምር በልበ ዝንጉዓን ያደረ ትምህርት አለ ። ወመጽኡ አዕዋፍ አጋንንት ያሳቱት አዕዋፍ አላቸው ለማሳት ይፈጥናሉና ። ኢትሕሚ ሰብእ ውስተ ቤትከ እስመ የፌ ሰማይ ያወፅእ ለነገርከ እንዲል

[illegible] ማለቱ የበሉት ደስ እንዲያሰኝ ሲያበቁ ደስ ይላቸዋልና ወቦ ዘወድቀ ዲበ ኰኩሕ ፈጥና ፀመቅቦ ተረጸሁ ከሚል ስፍሐ አእምሮ ከሌለው ልቡና ያደረ ትምህርት አለ እስመ አልቦ ስፍሐ አእምሮ ማለት ፕልቅ ዕውቀት የለውምና ። ወሶበ ሠረቀ ፀሐይ [illegible] በመጣበት ጊዜ ፈጥኖ የከደ [illegible] [illegible] ። ስፍሐ አእምሮ የለውምና ። ወቦ [illegible] ውስተ ሦክ ከባለቀቶች ልቡና ያደረ ትም ትምህርት አለ ። [illegible] ተምር ዐውቀ ሥራ እመ [illegible] ጊዜ እምነት ማፀሬት ያስተናብት ፣ ብዕል ሰፋጢት ማለት እንዲህ ብዕል ሐልዮ መንበርት ማለት [illegible] ማለል ትካዜ ዓለም ፍትረ ብእሲት ፍትረ ውሉድ ናቸው ፣ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ሠናይት በበጐ ልቡና ያደረ ትምህርት አለ [illegible] ወቦ [illegible] ወቦ [illegible] ሥራውን በሦስት ወገን ይመግባል በመሐይምነት በማእከላዊነት በፍጹምነት ከሁሉንም [illegible] ይወርሱታልና ፤ ባለ መቶ ባለ ስሳ ባለ ሠላሳ አለ ። እንድም ባለ መቶ ሰማዕታት ባለ ስሳ መነኰሳት ባለ ፴ በሕግ የጸኑ ሰብአ ዓለም ናቸው እንድም ሁሉም በሁሉ አሉ ብሎ ከሰማዕታት እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንደ ቂርቆስ እንደ ፋሲለደስ ያሉት ባለ መቶ ፤ ከነዚያ ዝቅ ያሉት ባለ ስሳ ከነዚያ ዝቅ ያሉት ባለ ሠላሳ ናቸው ። ከመነኰሳትም አቡነ ዕንጦንስ እንደ መቃርስ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ያሉት ባለ መቶ ከነዚያ ዝቅ ያሉት ባለ ስሳ ከነዚያ ዝቅ ያሉት ባለ ሠላሳ ናቸው ከሰብአ ዓለምም እንደ ኢዮብ እንደ አብርሃም ያሉት ባለ መቶ ከነዚያ ዝቅ ያሉት ባለ ፷ ከነዚያ ዝቅ ያሉት ባለ ፴ ናቸው ። አንድም ቦ ዘወድቀ ውስተ ፍኖት ፤ ፍኖት የተባለ መንግሥተ ሰማያት ድሉት ለጻድቃን ገሃነመ እሳት ድሉት ለኃጥአን እንደሆነች ተምሮ ዐውቆ ሥራ አስራለሁ ሲል አጋንንት ያስቀሩበት ነው ። ወቦ ዘወድቀ ዲበ ኰኩሕ ፣ ኰኩሕ የተባለ ካልተማሩ አያውቁ ካላወቁ አይጸድቁ እንዲሉ እማራለሁ አውቃለሁ ሲል ሳይማር ሳያውቅ የቀረ ነው ፤ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ሦክ ።

ሦክ የተባለ ትሩፋት አፍአዊን ሠርቶ ትሩፋት ስውርት የቀረችበት ነው ፣ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ሠናይት ምድር ሠናይት ያለው ሁሉንም የሠራ ነው ቦ ዘምእት ወቦ ዘስሳ ወቦ ዘሠላሳ፤ ይህም ወሥርዓተ ፍድፋዴ ዓለማውያን አስተጋብአ ሰገበ ሠለስቱ ክፍል እንዲል ሰማዕታትን በበጐ ልጅ መነኰሳትን በበጐ ሎሌ ሕጋውያንን በበጐ ባሕሪ መስሎ ይናገራል ። በጐ ልጅ አባቱ ሳለ ካባቱ ጋራ ይወጣል ይወርዳል አባቱ ከሞተ በኋላ ባባቱ ርስት ዘምቶ ይሞታል ፣ የሰማዕታት መደበኞች ሐዋርያት ናቸው በጐ ልጅ ካባቱ ጋራ እንዲወጣ እንዲወርድ ሐዋርያትም ጌታ ሳለ ከጌታ ጋራ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ሲወጡ ሲወርዱ ኑረዋል ። አባቱ ከሞተ በኋላ ባባቱ ርስት ዘምቶ እንዲሞት ጌታ ከሞተ በኋላ ወንጌልን ሲያስተምሩ በሰማዕትነት ሙተዋልና ፤ በጐ ሎሌም ጌታው ሽማ አጥበሀ ማገር ቆርጠሀ ና ያለው እንደሆነ ጌታዬ አይችልም ብሎ ነው እንጂ ልወጥ የሚሆን ንግ የሚማገርበት ልጥ ይገኝ ብሄድ ይከፋልን ብሎ ልብሱን አጥቦ ዓማውን ይዞ ማገሩን ቆርጦ ልጡን ጨምሮ ይዞ ይሄዳል ። መነኰሳትም ሚስት አግብታችሁ ዐሥራት በኩራት ቀዳምያት አውጥታችሁ እንግዳ ተቀብላችሁ ሥጋውን ደሙን በሚገባ ተቀብላችሁ ኑሩ ቢላቸው ባሕርያቸው ደካማ ነው አይቻላቸውም ብሎ ነው እንጂ ከሕገ ሥጋ ሕገ ነፍስ ከሕገ እንስሳ ሕገ መላእክት እንዲበልጥ ታውቆ የለም ብለው ከሴት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው ይኖራሉና በጐ ባሪያ የቆመውን ቁረጥ የተኛውን ፍለጥ ቢሉት ያዘዙትን ሁሉ ያደርጋል ። ሕጋውያንም ባዘዛቸው ትእዛዝ በሰራላቸው ሥራት ጸንተው ይኖራሉና ። ወእንዘ ዝሩት ይእቲ ማእከለ አድባር ወአውግር ወቆላተ ገዳም ተጋቢኦ ትከውን እሐተ ጽርስፎራ እንዲል መቶው ፣ ስሳው ፣ ሠላሳው ቅንጣት ተሰብስቦ አንድ ኅብስት እንዲሆን ሰማዕታትም መነኰሳትም ሕጋውያንም በማዕዘ ርትዕት አንድ ናቸው ።

፱ ዘቦ እዝነ ሰሚዕ ለይስማዕ

፱ ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ ማለት ፍኖት የተባለ በቁሙ ፍኖት እንዳይደለ ልበ ዝንጉዓን እንደሆነ ኰኩሕ የተባለ በቁሙ ኰኩሕ እንዳይደለ ስፍሐ አእምሮ የሌለው ልቡና እንደሆነ ሦክ የተባለ በቁሙ ሦክ እንዳይደለ ብዕል ሰፋጢት ሐልዮ መንበርት ያስቀሩበት እንደሆነ እዝነ ልቡና ያለው ያስተውል ።

፲ ወቀረቡ አርዳኢሁ ይቤልዎ በእንተ ምንት በምሳሌ ትትናገሮሙ ለሕዝብ ፤

፲ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው ለሕዝቡ በምሳሌ ስለምን ታስተምራቸዋለህ አሉት ።

፲፩ ወአውሥአ ወይቤሎሙ እስመ ለክሙ ተውህበ አእምሮ ምሥጢራቲሃ ለመንግሥተ ሰማያት፤

፲፩ የመንግሥተ ሰማይን ምሥጢር ማወቅ ለናንተ ተሰጥቷልና ማለት የወንጌልን ምሥጢር ማወቅ ለናንተ ተገልጧልና ። ወሎሙስ ኢተውሀበሙ ፤ ለሳቸው ግን አልተገለጸላቸውም ።

፲፪ እስመ ለዘቦ ይሁብዎ ። ማቴ ፳፭ ፣ ፳፱ ።

፲፪ ላለው ይሰጡታልና ማለት አእምሮ ላለው ይሁብዎ ምሳሌውን ይነግሩታልና ፤ ወይዌስክዎ ። ምሥጢሩን ይጨምሩለታልና ለከሙ ተውሀበ ላለው ወለዘሰ አልቦ እለሂ ቦ የኃይድዎ ። አእምሮ የሌለውን ግን ያለውን ይቀሙታልና ማለት እንዳያውቀው

ኢደርገው ይመስሉበታልና ለሙሰ ኢተውህበ ላለው እንድም ምሳሌውን ለያዘ ይሁብዎ ወይዌስክዎ እንድ ወገን ምሥጢሩን ትርጓሜውን ይነግሩታልና ስከሙ ቀ ተውህበ ላለው ወለዘሰ አልቦ ምሳሌውን ላልያዘ ግን ያለውን አእምሮውን ነሥተው በግእዚ እንስሳ ያቆሙታልና ወለሙሰ ኢተውህበ ላለው ።

፲፫ ወበእንተ ዝንቱ በአምሳል እትናገሮሙ ።

፲፫ ስለዚህ በምሳሌ እነግራቸዋለሁ እስመ
እንዘ ይሬእዩ ኢይሬእዩ ።
እናያለን ሲሉ አያዩምና ።
ወእንዘ ይሰምዑ ኢይሰምዑ ፤ እንሰማለን ሲሉ አይሰሙምና ወኢያለብዉ እናውቃለን ሲሉ አያውቁምና

፲፬ ከመ ይትፈጸም ላዕሌሆሙ ትንቢተ ኢሳይያስ ነቢይ ዘይቤ ፡ ኢሳ ፮፥፱ ። ማር ፬፥፲፪ ፡ ሉቃስ ፡ ፰፥፲ ፡ ዮሐ ፲፪፥፵ ። ግብ ፳፰፥፳፮ ፡ ፳፯ ፡ ሮሜ ፲፩ ፡ ፰ ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ።

፲፬ ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረው ትንቢት ባላቸው ይፈጸም ዘንድ ።
ሰሚዐ ትሰምዑ ወኢትለብዉ ማስማቱን ትሰማላችሁ አታስተውሉም ኢይሰምዑ ላለው ነጽሮተ ትኔጽሩ ወኢትሬእዩ ፤ ማየትን ታያላችሁ ማለት እናያለን ትላላችሁ አታስተውሉም ኢይሬእዩ ላለው ።
፲፭ እስመ ገዘፈ ልቡ ለዝ ሕዝብ
፲፭ አለዋቆች ሁነዋልና ።
ወእዘኒሆሙ ደንቀወ እምሰሚዕ የኢሳይያስ ቃል መፍቻ ፡ ጆሮቻቸው ከመስማት ደንቁረዋልና ኢይሰምዑ ላለው ።
ወክደኑ አዕይንቲሆሙ ከመ ኢይርአዩ በአዕይንቲሆሙ እንዳያዩ ዓይናቸውን ጨፍነዋልና ማለት ምሥጢር ከማየት ተከልክለዋልና ኢትሬእዩ ላለው ወበእዘኒሆሙ ኢይሰምዑ ። በጆሮቻቸው እንዳይሰሙ ወበልቦሙ ኢይሌብዉ ። በልባቸው እንዳያስተውሉ ከመ ኢይትመየጡ ኀቤየ ፤ ወደኔ እንዳይመለሱ ። ወኢይስሃሎሙ ይቅር እንዳልላቸው ።
፲፮ ወለክሙሰ ብፁዓት አዕይንቲክሙ ።
፲፮ ለናንተ ግን ሳይናችሁ ምስጋና ማለት እናንተ ግን ንዑዳን ክቡራን ናችሁ ።
እስመ ይሬእያ ። ያያሉና ማለት አይታችሁኛልና ።
ወእዕዛኒክሙ እስመ ይሰምዓ ። ጆሮቻችሁ ይሰማልና ማለት ሰምታችሁኛልና ንዑዳን ክቡራን ናችሁ ።
፲፯ እማን እብለክሙ ከመ ብዙኃን ነቢያት ወጻድቃን ፈተዉ ይርአዩ ዘትሬእዩ ወኢርእዩ ፡ ወፈተዉ ይስምዑ ዘትሰምዑ ወኢሰምዑ ሉቃ ፲ ፡ ፳፬ ።
፲፯ ብዙ ነቢያት ጻድቃን እናንተ የምታዩትን የምትሰሙትን ማለት ዛሬ የምትሰሙኝ የምታዩኝ እኔን ሊያዩኝ ሊሰሙኝ እንደ ወደዱ እንዳላዩኝ እዳንልሰሙኝ በእውነት እነግራችኋለሁ ። ሐተታ ነቢያት አላቸው ያበር የቸነፈር የጺዋዌን ነገር ተናግረዋልና ጻድቃን አላቸው እንደመጠናቸው ጥቂት ትሩፋት ሠርተዋልና ፤ ኢርእዩ ወኢሰምዑ አለ የሥጋዌ ነገር አልተገለጸላቸውምና ፡ አንድም ዶጋት አለ ኢሳይያስ እነ ኤርምያስ ናቸው ብሎ ወሰደችዋል ብዙ ነቢያት አላቸው ፡ የሥጋዌ ነገር ተገልጾላቸው ተናግረዋልና ጻድቃን አላቸው ብዙ ትሩፋት ሠርተዋልና እንዳላዩኝ እንዳልሰሙኝ አለ ገልጾላቸው ተናግረውት ዐረፍተ ዘመን ስገቷቸው ሳያዩት ቀርተዋልና ።

፲፰ ወአንትሙሰ ስምዑ ምሳሌሁ ለዘይዘርዕ
፲፰ እናንተስ የሚዘራውን ምሳሌ ስሙ ።

፲፱ ኵሉ ዘይሰምዕ ነገረ መንግሥተ ሰማያት ወኢይሌቡ ይመጽእ እኩይ ወይመሥጥ ቃለ ዘተዘርዓ ውስተ ልቡ ውእቱኬ ዘተዘርዓ ውስተ ፍኖት
፲፱ በመንገድ የወደቀው ዘር የመንግሥተ ሰማያት ነገር ሰምቶ የማያስተውለው እኩይ ዲያብሎስ መጥቶ ባልበናው የተዘራውን የሚያጠፋበት ነው ።
፳ ወዘሰ ውስተ ኰኵሕ ተዘርዓ ውእቱ ዘነገረ ይሰምዕ ወሶቤሃ በፍሥሓ ይትዌከፎ ።
፳ በቋጥኝ ላይ የወደቀው ዘር ነገሩን ሰምቶ ለጊዜው ደስ ብሎት የሚቀበለው ነው ።
፳፩ ወባሕቱ አልቦቱ ሥርው ላዕሌሁ ለጊዜሃ ዳዕሙ ውእቱ ወከዊኖሰ ምንዳቤ ወስደት በእንተዝ ነገር በጊዜሃ የዓሉ ።
፳፩ ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ ሥር የለውምና ስለዚህ ነገር መከራና ስደት በደረሰ ጊዜ ፈጥኖ ይክዳል ።
፳፪ ወዘሰ ውስተ ሦክ ተዘርዓ ዝ ውእቱ ዘነገረ ይሰምዕ ወትካዘ ዓለም ወስፍጠተ ብዕል ተሐንቆ ለነገር ወዘእንበለ ፍሬ ይከውን ።
፳፪ በእሾህ የተዘራው ዘር ነገሩን ሰምቶ የብልጽግና ማታለልና ይህን ዓለም ማሰብ አንቆት ያለ ፍሬ የሚሆን እሱ ነው ።
፳፫ ወዘሰ ውስተ ምድር ሠናይት ተዘርዐ ዝውእቱ ዘነገረ ይሰምዕ ወይሌቡ ወይፈሪ ወይገብር ።
፳፫ በበጐ ምድር የተዘራው ዘር ግን ነገርን ሰምቶ የሚያስተውለው የሚሠራው ነው ።
ቦ ዘምእት ወቦ ዘ፷ ወቦ ዘ፴ ። መቶ ስሳ ሠላሳ የሚያፈራ አለ ።

በእንተ ምሳሌ ዘሥርናይ ሠናይ ወዘክርዳድ ።

፳፬ ካልዕተ ምሳሌ አምጽአ ሎሙ ። ማር ፬፥፳፮
፳፬ ሁለተኛ ምሳሌ ሌላ ምሳሌ መሰሎ ነገራቸው
እንዘ ይብል ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብእሴ ዘዘርዓ ሠናየ ዘርዓ ውስተ ገራኁቱ ።
መንግሥተ ሰማያት ሕገ ወንጌል ፡ ሕገ ወንጌል ተሰፋ ተሰፋ ኢየሱስ ክርስቶስ የተበጠረ የተንጠረጠረ

ዘርን የሚዘራ ገበሬን ትመስላለች ። ገራኅት ይህ ዓለም ፣ አንድም መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ትመስል ዘርዓ በል ፣ ገበሬ በርሻው የሚዘራት የተበጠረ የተንጠረጠረ ዘርን ትመስላለች ገራኅት ልቡና ።

፳፭ ወእንዘ ይነውሙ ሰብእ መጽአ ጸላኢሁ ወዘርአ ክርዳደ ማእከለ ሥርናይ ወኀለፈ ።

፳፭ ሰዎች ተኝተው ሳሉ ጠላት መጥቶ በስንዴው መካከል ክርዳድ ዘርቶ ሄደ ።

፳፮ ወሶበ በቈለ ሥርናይ ወፈረየ አሜሃ አስተርአየ ክርዳድኒ ።

፳፮ ሥንዴው በበቀለና ባፈራ ጊዜ ያን ጊዜ ክርዳዱም ታየ ማለት ተለይቶ ታወቀ ።

፳፯ ወመጺኦሙ አግብርቲሁ ለበዓለ ገራኅት ይቤልዎ እኮሁ ሠናየ ዘርአ ዘራዕከ ውስተ ገራኅትከ

፳፯ ብላቴኖቹ መጥተው ባለቤቱን አቤቱ በርሻህ በጎ ዘር ዘርተህ አልነበረምን ። እምአይቴ እንከ ሎቱ ክርዳድ ክርዳድ ከወዴት ተገኘ አሉት ።

፳፰ ወይቤሎሙ ብእሲ ፀራዊ ገብረ ዘንተ ።

፳፰ ጠላት ሰው ይህን አደረገ ። አንድም ዕጓለ ፀራዊ ደላል የጠላት ልጅ እንዲህ አደረገ ወአግብርቲሁ ይቤልዎ ትፈቅድኑ እንከ ንሑር ወንጸሐይዮ ብላቴኖቹም ሄደን ክርዳዱን ነቅለን ልንጥለው ትወዳለህን አሉት ።

፳፱ ወይቤሎሙ አልቦ ።
አይሆንም አላቸው ።

፳፱ ከመ እንዘ ተዓርዩ ክርዳደ ኢትምሕውዎ ምስሌሁ ሥርናየኒ ።
ክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ ሥንዴውን እንዳትነቅሉ

፴ ኅድግዎ ይልሐቁ ኅቡረ እስከ ጊዜ ማዕረር

፴ ተዋቸው እስከ መከር ድረስ ባንድነት ይኑሩ ወበጊዜ ማዕረር እብሎሙ ለእለ የዐጽዱ ርእዩ ቅድመ ክርዳደ ወእሰርዎ በበከላስስቲሁ ወአውዕይዎ በእሳት መከር በደረሰ ጊዜ የሚያጭዱትን አስቀድማችሁ ክርዳዱን ከሥንዴው አይታችሁ በየነዶው አስራችሁ በእሳት አቃጥሉት ።
ወሥርናዮሰ አስተጋብኡ ውስተ መዛግብትየ ።
ሥንዴውን ግን በጎታ በጎተራ በሪቅ ሰብስቡት አላቸዋለሁ ። አንድም ወእንዘ ይነውሙ ሰብእ ብለህ መልስ ። ሐዋርያት ካለፉ በኋላ ዲያብሎስ አርዮስን ሦስቱ ምእት ካለፉ በኋላ መቅዶንዮስን መቶ አምሳው ካለፉ በኋላ ንስጥሮስን ማምነሣቱ መናገር ነው ወሶበ በቈለ በተሾመ ባስተማረ ጊዜ ክህደቱ ኑፋቄው ተገልጾ ታወቀ ። ደቀ መዝሙር ከመምሩ ቤት ሳለ ክህደቱን ኑፋቄውን አይገልጸውምና ፣ ወመጺኦሙ አግብርቲሁ መላእክት ቀርበው እምጸኤ ዓለማት ፈጣሬ ዓለማት ጌታችን አቤቱ በዚህ ዓለም በጎ ትምርት አስተምረህ አልነበረምን ፣ እምአይቴ እንከ ሎቱ ክርዳድ ፤ ይህ ክህደት ኑፋቄ ከወዴት መጣ አሉት ። ወይቤሎሙ ፀራዊ ገብረ ዘንተ ፣ ኢላፊ ዲያብሎስ እንዲህ አደረገ አንድም የጠላቱ የዲያብሎስ የግብር ልጁ መናፍቅ እንዲህ አደረገ ። ሰው በባሕርዩ እንዲራባ እሱም በግብር ይራባልና ፣ ሐተታ መላእክት የሚጠይቁት ጌታ የሚመልስላቸው ሁኖ አይደለም ። በዚህ ዓለም በጎ ትምርት አስተምሮ አልነበረም ይህ ክህደት ኑፋቄ ከወዴት ተገኘ ብለው በመረመሩ ጊዜ ክህደት ኑፋቄ የተገኘ ከዲያብሎስ እንደሆነ የሚያውቁበትን ዕውቀት ከሱ ማግኘታቸውን መናገር ነው ። ወአግብርቲሁስ ይቤልዎ ትፈቅድኑ ንሑር ንጸሐይዮ ። ኃጥኡን ከጻድቅ ለይተን ልናጠፋው ትወዳለህ አሉት ፣ ወይቤሎሙ አልቦ አይሆንም ከመ እንዘ ትጸሐይዩ ኃጥኡን እናጠፋለን ስትሉ ጻድቁን እንዳታጠፉ የኀጥኡ ዳፋ ጻድቁን ይዳፋ እንዲሉ ፣ ለይቶ ማጥፋት ይቻላቸው የለም ፣ ይህም በኖኅ በሎጥ ታውቋል ብሎ ከነዚህ የሚወለዱ በንስሐ የሚመለሱ ብዙ አሉና ፣ ኅድግዎሙ ተዋቸው እስከ ዕለተ ምጽአት ባንድነት ይኑሩ ። ወበጊዜ ማዕረር ፣ ምጽአት በደረሰ ጊዜ መላእክትን አዛቸዋለሁ ። ርእዩ ቅድመ ። አስቀድማችሁ ኃጥአንን ከጻድቃን ለይዋቸው ። ወእሰርዎ በበከላስስቲሁ ፣ በየወገናቸው በገሃነም ሥቃይ እምጡባቸው ወሥርናዮሰ ጻድቃንን ግን በመንግሥተ ሰማይ አኑሯቸው አላቸዋለሁ ። ሐተታ መዛግብት አላት በብዙ ወገን ትመሰላለችና ፣ እስመ ውስተ ቤተ አቡየ ብዙኅ ማኅደር ወምዕራፍ ቦቱ እንዲል ፣ አንድም ትመስል ብለህ መልስ ። መንግሥተ ሰማይ ሊቀ ማኅበር በርሻው የተበጠረች የተንጠረጠረች ዘርን የሚዘራ ገባሬን ትመስላለች ገራኅት ኀዳም ፣ አንድም መንግሥተ ሰማይ ሥርዓተ ማኅበር ፣ ገበሬ በርሻው የዘራት የተበጠረች የተንጠረጠረች ዘርን ትመስላለች ። ገራኅት ልቡና ፣ ወእንዘ ይነውሙ አበው ሥርዓት ሠርተው ካለፉ በኋላ ዲያብሎስ ክፉ ሕሊና ማምጣቱን መናገር ነው ። ወሶበ በቈለ ፣ ሥራ እሠራለሁ ባለ ጊዜ ክፉ ሕሊና ተለይቶ ታወቀ ወመጺኦሙ መላእክት ቀርበው ጌታን ለሰው በጎ ሕሊናን ፈጥረህለት አልነበረምን ይህ ክፉ ሕሊና ከወዴት ተገኘ አሉት ብእሲ ፀራዊ ጠላቱ ዲያብሎስ እንዲህ አደረገ አላቸው ። ሐተታ መላእክት የሚጠይቁት እሱም የሚመልስላቸው ሁኖ አይደለም ። ለሰው በጎ ሕሊና ፈጥሮለት አልነበረም ይህ ክፉ ሕሊና ከወዴት ተገኘ ብለው በመረመሩ ጊዜ ክፉ ሕሊና የሚገኝ ከዲያብሎስ እንደ ሆነ የሚያውቁትን ዕውቀት ከጌታ ማግኘታቸውን መናገር ነው ። ወአግብርቲሁስ መላእክት ክፉውን ሕሊና ልናጠፋው ትወዳለህን አሉት ፣ ወይቤሎሙ አልቦ ፣ አይሆንም እስመ እንዘ ተአርዩ ክፉውን ሕሊና እናጠፋለን ስትሉ በጎውን ሕሊና

እንዲታዉቃ ፡ ኅድግዎሙ ቲዋቸው እስከ ተባሕትዎ ድረስ ሞኝድነት ይኑሩ ። ወበጊዜ ማዕረር ። በተባሕትዎ ጊዜ ሥርዓት የሚሠሩ አበውን አዛቸዋለሁ ፤ አስቀድማችሁ ክፉውን ሕሊና ከበጐው ሕሊና ለይታችሁ በየአገባቡ በቀኖና እርቁት ። ወሥርናዩሰ በጐውን ሕሊና ግን በመንፈስ ቅዱስ አሰጠብቁት አላቸዋለሁ ። መዛግብት አለው መንፈስ ቅዱስን ስለ ሀብቱ ብዛት ።

በእንተ ምሳሌ ዘሕጠተ ሰናፔ ።

፴፩ ካልዕተ ምሳሌ አምጽአ ሎሙ ሁለተኛ ምሳሌ ፡ ሌላ ምሳሌ መሰለላቸው ። ማር ፬ ፴፩ ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱

፴፩እንዘ ይብል ትመስል መንግሥተ ሰማያት ኅጠተ ሰናፔ እንተ ተነሥአ ብእሲ ወዘርዓ ውስተ ገራኅቱ ። መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ፤ ሕገ ወንጌል ተስፋ ተሰፋ ኢየሱስ ክርስቶስ በርሻው የሰናፍጭ ቅንጣት የሚዘራ ገበሬን ትመስላለች ። ገራኅት ይህ ዓለም ። አንድም መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ገበሬ በእርሻው የዘራት ሰናፍጭን ትመስላለች ገራኅት ልቡና ። ሐተታ ሰናፍጭ ፍጽምት ናት ነቅ የለባትም ወንጌልም ነቅዓ ኑፋቄ የለባትምና ። ሰናፍጭ ላይዋ ቀይ ውስጧ ነጭ ነው ። ወንጌልም በላይ ደማችሁን አፍሱ ትላለች በውስጥ ግን ሕገ ተስፋ ናትና ፡ አንድም ሰናፍጭ ጣዕሟ ምሬሯን ያዘነጋዋል ፤ ወንጌልም ተስፋዋ መከራዋን ያዘነጋዋልና ። አንድም ሰናፍጭ ቁስለ ሥጋን ታደርቃለች ። ወንጌልም ቁስለ ነፍስን ታደርቃለችና ። አንድም ሰናፍጭ ደም ትበትናለች ወንጌልም አጋንንትን መናፍቃንን ትበትናለችና ። አንድም ከምትደቁስበት ተሐዋስያን አይቀርቡም ። ወንጌልም ከምትነገርበት አጋንንት መናፍቃን አይቀርቡምና ። ሰናፍጭ ስትደቁስም ስትበላም ታስለቅሳለች ። ወንጌልም ሲማሯትም ሲያስተምሯትም ታሳዝናለችና ። ሰናፍጭ ከበታችዋ ያሉትንም አታክልት ታመነምናለች ፡ ወንጌልም የመናፍቃንን ጉባኤ ታጠፋለችና ። ሰናፍጭ አንድ ጊዜ የዘሯት እንደ ሆነ ባመት ባመት ዝሩኝ አትልም ተያይዛ ስትበቅል ትኖራለች ። ወንጌልም በመቶ ሃያ ቤተሰብ ተጀምራ እስከ ምጽአት ድረስ ስትነገር ትኖራለችና ።

፴፪ ወይእቲ ትንእስ እምኵሉ አዝርዕት ።

፴፪ ስትዘራ ከአዝርዕት ሁሉ ታንሳለች ።

ወሶበ ልህቀት ተዓቢ እምኵሉ አሕማላት ።

ባደገች ጊዜ ግን ከአዝርዕት ሁሉ ትበልጣለች ፤ እንደሷ ካሉ ከሾፍ ዘር ከኀመን ዘር ። ወትከውን ዕፀ ዐቢየ ። ደግ ዕፅ ትባላለች ።

እስከ ይመጽኡ አዕዋፈ ሰማይ ወያጸልሉ ታኅተ አዕጹቂሃ ። አዕዋፍ መጥተው ማረፊያ መሰፈሪያ ዛፍ እስኪያደርጓት ድረስ ። አንድም ወይእቲ ትንእስ ብለህ መልስ ። ወንጌል ስትነገር ከሁሉ ታንሳለች በመቶ ሐያ ቤተ ሰቡ መዠመሯን ትንእስ አለ ፤ በጉባኤ በተነገረች ጊዜ ግን ከሕገጋት ሁሉ ትበልጣለች ። ወትከውን ፡ ደግ ሕግ ትሆናለች ፤ ወይመጽኡ ሕዝብ አሕዛብ አስኪያምኑባት ድረስ ። አንድም ትመስል ብለህ መልስ ። በጥምቀት በተአምኖ ኃጣውእ ያሉ ሰዎች በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ያሉ ሰዎችን ይመስላሉ ። ወይእቲ ትንእስ ፡ በጥምቀት የሚሰጠው ጸጋ በመጠኑ ነውና ፡ ትንእስ አለ ያም ኃጢአቱን ሲናገር ተዋርዶ ነውና ። ወሶበ ልህቀት ፤ በጥምቀት ያገኘውን ጸጋውን በሥራ ባስፋው ጊዜ ያም ቀኖናውን በፈጸመ ጊዜ ከሰው ሁሉ ይበልጣል ። ወትከውን ። ደግ ሰው ይባላል ፤ ወይመጽኡ ሰው ሁሉ መጥቶ ከእግሩ ወድቆ አትርሳኝ እስኪለው ድረስ ።

በእንተ ምሳሌ ዘብሑእ ።

፴፫ ካልዕተ ምሳሌ ነገሮሙ ። ሉቃ ፲፫፡ ፳፩ ።

፴፫ ሰቀረበው ካልዕት ይላል ሁለተኛ ምሳሌ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው ።

ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብሑአ ዘነሥአት ብእሲት ወአብኀአቶ ውስተ ሠለስቱ መሥፈርተ ሐሪጽ መንግሥተ ሰማያት እንዳለፈው ፤ በሦስት መሥፈሪያ ዱቄት የሸሸገችው ማለት ሦስት መስፈሪያ ዱቄት የለወሰችበትን ሴት የያዘችውን ።

ወአብኀአ ኵሎ ።

ሁሉን ወደ ምጸት የሳበ እርሾን ትመስላለች ። ብኁእ ጌታ ብእሲት ጥበቡ ውስተ ሠለስቱ መሥፈርተ ሐሪፅ ፤ ሥጋን ነፍስን ደመ ነፍስን ያዋሐደችው ። ወአብኀአ ኵሎ በተዋሕዶ ሥጋን የባሕርይ አምላክ ማድረጉን መናገር ነው ። አንድም ብእሲት መምህራን ብኁእ ወንጌል ፡ ውስተ ሠለስቱ ወንጌል መሠራቷ ለሦስቱ ነገድ ነውና ለነገደ ሴም ለነገደ ያፌት ለነገደ ካም፡ወአብኀአ ኵሎ በወንጌል ሁሉ መክበሩን መናገር ነው ። አንድም ብእሲት መምህራን ብሑአ ጥምቀት ፤ ውስተ ፫ቱ ፤ ጥምቀት በሦስቱ ስም ነውና ወአብኀአ ኵሎ በጥምቀት ሁሉ መክበሩን መናገር ነው ። አንድም ብእሲት ቀሳውስት ብኁእ ፤ ሥጋው ደሙ ፤ ውስተ ሠለስቱ ። ለቀድሶተ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ ብሰው ይሰጣሉና ወአብኀአ ኵሎ ፤ በሥጋው በደሙ ሁሉ መክበሩን መናገር ነው ። አንድም ብእሲት ቡርከት ነፍስ ፤ ብኁእ ጸጋ ጥምቀት ውስተ ፫ቱ መሥፈርተ ሐሪፅ ውስተ ፫ቱ መክፈልተ ሕሊናሃ እንዲል ፡ ሥራውን በሦስት ወገን ትሠራዋለች በወጣኒነት በማእከላዊነት በፍጹምነት ክብሩንም በዚያው ልክ ትወርሰዋለችና ፤ ወአብኀአ ኵሎ ። በሥራው ሁሉ መክበሩን መናገር ነው ፤ አንድም ብኁእ ጌታ ብእሲት ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ። ውስተ ሠለስቱ ፡ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር መኖሩን

መናገር ነው ። ወእብነኒ ሁሉ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ አንድ ወገን ሁኖ መንግሥቱን መናገር ነው ።

፴፬ ወዘንተ ኵሎ ተናገረ እግዚእ ኢየሱስ በምሳሌ ለአሕዛብ ። ማር ፬ ፥ ፴፫ ።

፴፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአሕዛብ ይህን ሁሉ በምሳሌ አስተማራቸው ።
ወዘእንበለ በምሳሌ ኢተናገሮሙ ።
ያለ ምሳሌ ግን አላስተማራቸውም አለ በዚህ ቀን አንድም በሆነ ምሳሌ እንጂ ባልሆነ ምሳሌ አላስተማራቸውም ።

፴፭ ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ በነቢይ እንዘ ይብል እከሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር አምሳለ ዘእምትካት ።

፴፭ መዝ ፸፯ ፥ ፪ አፉን ምሳሌ አገልጣለሁ የተሰወረውን ምሳሌ አስተምራለሁ ብሎ በነቢይ የተነገረው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ። በከመ ይቤ አሳፍ የሚል አብነት ይገኛል ሰዳዊት ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት መዘምራን ነበሩት አለቆቻቸው አሳፍ ቆሬኤማን ኤዶትም ይባላሉ በየአለቆቻቸው ካሬት ተከፍለው ዐሥራ ሁለት ዐሥራ ሁለት እየሆኑ ወገን አራቱ ጊዜ ይጸልያሉ ።
ልክ ናቸው እሱም ከደባባይ በማይወጣበት ነገር በማይወጣበት ጊዜ እየገባ ይጸልያል ሥራ መፍቻት የሰም በዚህ ጊዜ አጽምዎ ለአሳፍ ደርሶት ነበርና ስለዚህ በከመ ይቤ አሳፍ የሚል አብነት ይገኛል ።

በእንተ ፍካሬ ዘምሳሌ ክርዳድ ።

፴፮ ወእምዝ ኅደጎሙ ለአሕዛብ ወቦአ ውስተ ቤት ።

፴፮ ከዚህ በኋላ ሕዝቡን በአፍአ ትቶ ከቤት ገባ ወቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ ። ደቀ መዛሙርቱም ወደሱ ቀረቡ ወይቤልዎ ፈክር ለነ ምሳሌ ዘክርዳድ ወዘገራህት ።
በክርዳድ በገራህት የመሰልከውን ተርጕመህ ገልጸህ ንገረን አሉት እንደ ከተማ ደቀ መዝሙር አይደሉምና የከተማ ደቀ መዝሙር ቢያየውም ባያየውም ዝም ብሎ ይሄዳል ።

፴፯ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ዘይዘርዕ ሠናየ ዘርዓ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ውእቱ ።
፴፯ ያ መልካም ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው ብሎ መለሰላቸው ።
፴፰ ወገራህትኒ ዓለም ውእቱ ፤
፴፰ እርሻውም ዓለም ነው ።
ወሠናይኒ ዘርዕ ውሉደ መንግሥት እሙንቱ ።
መልካም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው ።
ወክርዳድኒ ውሉዱ ለእኩይ ።
ክርዳዱም የክፉ ልጆች ናቸው ።

፴፱ ወፀራዊኒ ዘዘርዖ ዲያብሎስ ውእቱ ።
፴፱ ራእ ፲፬ ፡ ፲፭ ። የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው ።
ወማዕረርኒ ኅልቀተ ዓለም ውእቱ ።
መከሩም የዓለም ፍጻሜ ነው ወዓጻድኒ መላእክት እሙንቱ አጫጆችም መላእክት ናቸው ።

፵ ከመኬ የዓርይዎ ለክርዳድ ቅድመ ወያውዕይዎ በእሳት ።

፵ ክርዳዱን አስቀድመው መርጠው በእሳት እንዲያቃጥሉት ፤ ከማሁ ይከውን በኅልቀተ ዝንቱ ዓለም ።

በዚህ ዓለም ፍጻሜ እንዲህ ይሆናል ።

፵፩ ይፌንዎሙ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ለመላእክቲሁ ።
፵፩ የሰው ልጅ መላእክትን ያዛቸዋል ።
ወየዓርዩ እመንግሥቱ ኵሎ ዓላውያን ወእለ ይገብሩ አበሳ በደል የሚያደርጉትንና ወንጀለኞችን ከመንግሥቱ ላይ ለይተው ።
፵፪ ወይወድይዎሙ ውስተ እቶነ እሳት ኀበ ሀሎ ብካይ ወሐቅየ ሥነን ።
፵፪ ልቅሶ ጥርስ ቁርጥማት ወዳለበት እቶን እሳት ይጨምሯቸዋል ።
፵፫ አሜሃ ይበርሁ ጻድቃን ምስብዒተ እደ እምብርሃነ ፀሐይ በመንግሥተ አቡሆሙ ።
፵፫ ጥበ ፫ ፥ ፯ ። ዳን ፲፪ ፥ ፫ ። ያን ጊዜ ጻድቃን ሰማያዊ አባታቸው በሚያወርሳቸው በመንግሥተ ሰማይ ከፀሐይ ሰባት እጅ ያበራሉ ።
ዘቦ እዝነ ሰሚዕ ለይስማዕ ። ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ ማለት እዝነ ልቡና ያለው ያስተውል ።

በእንተ መድፍን ወባሕርይ ወገሬፍ ።

፵፬ ወካዕበ ትመስል መንግሥተ ሰማያት መድፍነ ዘኅቡዕ ውስተ ገራህት ።
፵፬ ለቀረበው ካዕበ ይላል ሁለተኛ መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ሕገ ወንጌል ተሰፋ ፡ ተሰፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኅቡእ ዝጉብ ይላል በእርሻ ውስጥ የተቀበረች ወርቅን ትመስላለች ። ወረኪቦ ብእሲ ኀብኦ ሰው አግኝቶ የሰወራትን ፤ ወእምፍሥሐሁ ሖረ ወሤጠ ኵሎ ዘቦ ወተሣየጣ ለይእቲ ገራኅት ፤ ከደስታው የተነሣ ሂዶ ያለ ገንዘቡን ሸጦ ያቺን እርሻ የገዛላትን ። ሐተታ ምድሩን ካልገዛሁ ወርቁን አላገኝም ብሎ ባልሆነ ምሳሌ አያስተምርምና የኢዮምያስ ሰዎች የቀበሩት ወርቅ ነው ። አንድም ካዕበ ትመስል መድፍነ ብለህ መልስ ብእሲ ጌታ መድፍን አዳም ገራኅት ይህ ዓለም ነው ፤ ወረኪቦ ጌታ አዳምን በዚህ ዓለም ንስሐ ገብቶ ባገኘው ጊዜ ባሕርየ አዳምን ባሕርየ አድርጎ አዳምን ማዳኑን መናገር ነው ። እንዓሥእ ለዘንሥእ እመላእክት ዘእ

ንበለ ዳዕሙ እምዘርአ አብርሃም እንዲል ። አንድም ብእሲ ዮሴፍ ሠድፉን ጌታ ገራኅት እመቤታችን ፤ ዮሴፍ ጌታን እመቤታችንን ባገኛቸው ጊዜ ቤቱን ንብረቱን ትቶ ተከትሎ ግብጽ መውረዱን መናገር ነው አንድም ብእሲ ሐዋርያት መድፋን ጌታ ገራኅት ይህ ዓለም ወረኪቦ ሐዋርያት ጌታን በዚህ ዓለም ባገኙት ጊዜ መረባቸውን መርከባቸውን ትተው ጌታን መከተላቸውን መናገር ነው፡፡አንድም አምስቱን ግብራትባም ስቱ ግብራት ተሰውረው ባገኛቸው ጊዜ ትፍሥሕትን በኃዘን ኃይልን በድካም ብዕልን በንዴት ልዕልናን በትሕትና ግዕዛንን በግብርናት ተሰውረው ባገኛቸው ጊዜ ትፍሥሕቱን ለኃዘን ኃይሉን ለድካም ብዕሉን ለንዴት ልዕልናውን ለትሕትና ግዕዛኑን ለግብርናት ሰጥቶ አዳምን ማዳኑን መናገር ነው ። አንድም ምእመናን አምስቱን ግብራት ገንዘብ ማድረጋቸውን መናገር ነው ። አምስቱ ግብራት የተባሉ ፤ ዓለም ተውላጠ ዓለም ምግባር መንፈሳዊ ቃለ መጻሕፍት ቃለ መምህራን ናቸው ። ዓለም ይህ ዓለም ነው ሁሉ የሚገኝ ከዓለም ነውና ፤ ተውላጠ ዓለም እንደ የዋህ ጳውሊ ባለጸጋ አባት ነበረው አባቱ ሙቶ በገንዘብ ከወንድሙ ጋራ ተጣልቶ ወደ ዳኛ ሲሄድ እንዳባቱ ያለ ባለጸጋ ሙቶ ወደ መቃብር ሲወስዱት አገኘና ይህ ምንድነው ብሎ ጠየቀ ባለጸጋ ነበር ሙቶ ሊቀብሩ ይወስዱታል አሉት ። ለዚህ ብየ ከወንድሜ ተጣላሁን አንተን ይምሰል ብሎ ጥሉለት ሄዷል ። ምግባር መንፈሳዊ እንደ አብርሃም መርዓዊ ነው እድ ብርሀት ከጫጉላው እፁጥታ እየመራች ገዳም ወስዳዋለች ቃለ መጻሕፍት እንደ አባ ዕንጦንስ ምንተ ይብቁዖ ለሰብእ ለእመ ዘኮሎ ዓለመ ረብሐ ወኅጕለ ኃጕለ የለውን ይዞ መንኖ ሄዷል።ቃለ መምህራን እንደ አትናስዮ፤ምእመናንን የምትረዳ ደግ ሴት ነበረች ሰይጣን በዝሙት ድል ነሣት ምእመናንን የማትጠይቃቸው ሆነ ሰይጣን ልጃችንን ቀማን በተቻለህ ርዳን ብለው ከዮሐንስ ሐጺር ላኩ ሂዶ ንገሩልኝ አለ ነገሩለት ግባ በሉት አለች ገባ አስነጥፋ ና ከጠገቤ ተቀመጥ አለችው በወንበር ከፊቷ ተቀምጦ እያያት ያለቅስ ጀመር ምነው ታለቅሳለህ አለችው መልከ መልካም ነሽና ብታሳዝኝኝ ነው አላት ይህማ ደስ ያሰኛል እንጂ ያሳዝናል አለችው መፍረስ መበስበስ አለና ምን ይሆናል አላት ለዚህ ምን ይበጃል አለችው ብትተይው አላት ብተወው ጌታዬ ይምረኛል አለችው ይምርሻል አላት አንድም እሱ በገባ ጊዜ ሲያሰስ ንዋት የነበሩ አጋንንት መብራት እንደ አበሩባቸው አርጋብ ሲወድቁባት ሲነሱባት አየ እንዲህ ሲሆኑ ብሽ አየሁ አላት ለዚህም ይበጀኛል አለችው ብትተይው ብተወው ጌታዬ ይምረኛልን አለችው አምን ይምርሻል ተከተይኝ ብሏት ወጣ አብራው ወጣች አባቱ ቆየኝ ትለዋለች ድረሽብኝ ይላታል አ ግሯ አልችል ቢል ከልብሷ እየቀደደች አንደ ጫማ እያደረገች ትከተለዋለች ። አባቴ ቆየኝ ትለዋለች ድረሽ ይላታል ከጥታው ደርሶ አሳቁን አንድዶላት ተቀመጠች እሱ አልፍ ብሎ ጸሎቱን ያዘ በዚያ ሌሊት ዐረፈች ሰዋስወ ብርሃን ተተክሎ መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ያያል ማዕርጉ ጽግዌ ነውና የተላኩበትን ግን አያውቅም ሲነጋ መልአክ መጥቶ ያች ያመጣሃት ሴት ዐርፋለች መቃብሯን አንበሳ ይቆፍርልሃልና ቅበራት አለው ይህስ ይሁን ዛሬ ሌሊት ስትወጡ ስትወርዱ ያየኋችሁ ምንድን ነው አለው ነፍሷን ስናሳርግ ነው አለው ተቀበላትን አለው እዎን ተከተይኝ ብለሃት ተከትላህ በወጣች ጊዜ ተጋድገ ለኪ ብሏታል ብሎ ነግሮታል ።

፵፭ ካዕበ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብእሴ ሠያጤ ዘየኃሥሥ ባሕርየ ሠናየ ።

፵፭ መንግሥተ ሰማያት ሕገ ወንጌል ሕገ ወንጌል ተሰፋ፤ተሰፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ብሩሃ ሲል ነው ዕንቍን የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች ።

ወረኪቦ አሐተ ባሕርየ እንተ ብዙኅ ሤጣ ሖረ ወሤጠ ኵሎ ዘቦ ወተሣየጣ ።

ዋጋዋ ብዙ የሆነ ዕንቍን ባገኘ ጊዜ ያለ ገንዘቡን ሽጦ የገዛትን ብእሲ ጌታ ዕንቍ አዳም፤አዳምን ንስሐ ገብቶ ባገኘው ጊዜ ባሕርዩን ባሕርይ አድርጎ አዳምን ማዳኑን መናገር ነው ። አንድም ብእሲ ጌታ ዕንቍ አዳም መንግሥት ሰማይ ሐዋርያት አዳምን የሚሻ ጌታን ይመስላል ።

አንድም መንግሥተ ሰማይ ምእመናን ጌታን የሚሹ ሐዋርያትን ይመስላሉ ፤

ሐዋርያት የሚሹት ጌታን ይመስላሉ ።

፵፯ ካዕበ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ገሪፈ እንተ ተወድየት ።

፵፯ ውስተ ባሕር ወአስተጋብአት እምኵሉ ዘመደ ዓሣት ።

፵፯ መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ሕገ ወንጌል ተሰፋ፤ ተሰፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕር ላይ

፵፯ የጣሏትን ዓሣን ሁሉ ሰብስባ የያዘች ዘረመትራንን ትመስላለች ።

፵፰ ወሶበ መልአት አዕርግዋ ውስተ ሐይቅ

፵፰ በመላች ጊዜ ከወደቡ ያወጧትን

ወነቢሮሙ ኅረዩ ሠናዮ ወወደዩ ውስተ ሙዳዮሙ ። ከወደቡ ተቀምጠው ደጋጉን እየመረጡ ከማጥናቸው አኖሩ ። አረዩ ኃረዩ በየኑ ቤጹ ይላል ወእኩዮሰ ገደፍዎ አፍአ ፤

ከፉውን ግን መልሰው ከባሕር ጣሉት አጿራግዛራስ ከብዶ ይባላል ።

፵፱ ከማሁ ይከውን በኅልቀተ ዓለም

፵፱ በዕለተ ምጽአት እንዲህ ይደረጋል ።

፶ ወይወጽኡ መላእክት ወይፈልጡ ኃጥአነ እማእከሎሙ ለጻድቃን ወይወድይዎሙ ውስተ እቶነ እሳት ኀበ ሀሎ ብካይ ወሐቅየ ስነን።

፶ መላእክት መጥተው ጻድቃንን ለይተው በመንግሥተ ሰማይ ያኖሯቸዋል ፥ ኃጥአንን ከጻድቃን ለይተው ልቅሶ ጥርስ ቊርጥማት ባለበት በገሃነም ያኖሯቸዋል ። አንድም ትመስል ገሪፈ ብለህ መልስ ገሪፍ ወንጌል ብሔሩ ሙሉ ዓለም ። ወአስተጋብአት ፡ ሕዝቡን አሕዛቡን አንድ ያደረገች። ወሶበ መልአት ይህ ዓለም የሚያልፍ ጻድቃን በነገደ ዲያብሎስ ልክ ሲሞሉ ነውና ። አንድም ገሪፍ ሥርዓተ ማኅበር ባሕር ዓለም ። ወአስተጋብአት ሰውን ሁሉ የሰበሰበች ወሶበ መልአት ብዙ ዘመን ከረዳ በኋላ ትዛሕትም ያዝ ይሉታል ። በ፫ በ፯ ፱ በ፲ ምልክት ይታይለታል ፤ በ፩ኛው በ፫ኛው በ፲ኛው ተባሕትዎ ይይዛል ምልክት ባይታይለት የረዳበት ዘመን ተቈጥሮ ይይዛል ምልክት ለሁሉ አይታይምና ወእኩየሰ ሳይረዳ ተባሕትዎ እይዛለሁ ያለውን ግን ገና ነህ ርዳ ይሉታል ወያወፅእዎ ዘበአንሥሮት እንዲል ። ከማሁ ይከውን በህልቀተ ዝንቱ ዓለም።በዕለተ ምጽአት እንዲህ ይደረጋል ።

፶፩ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለበውክሙኑ እንከ ዘንተ ኵሎ ።

፶፩ ጌታ ይህን ሁሉ ዐወቃችሁት አላቸው ። ሐተታ እንደ ከተማ መምህር አይደለምና የከተማ መምህር ቢያውቁትም ባያውቁትም ዝም ብሉ ይላል ።

ወይቤልዎ እወ ፤

አዎን አሉት ፤ እሳቸውም እንደ ከተማ ደቀ መዝሙር አይደሉምና ያወቁትን አዎን ያላወቁትን ፈከር ለኝ ይሉታልና ።

፶፪ ወይቤሎሙ በእንተ ዝንቱ ኵሉ ጸሐፊ ዘይፀመድ ለመንግሥተ ሰማይ ይመስል ብእሴ በዓለ ቤት ዘያወፅእ እመዝገቡ ሐዲሰ ወብሉየ ።

፶፪ ስለዚህ ነገር ወንጌልን የሚያስተምር ሁሉ አሮጌና አዲስ ከሣጥኑ የሚያወጣ ማለት ልብስ ያለውን የማያጣ ባለጸጋን ይመስላል ። ልጥቀስ ቢል አያጣም ። አንድም አዲሱን ለመልበስ ብሉዩን ለማናፈስ ከሣጥኑ የሚያወጣ ባለጸጋን ይመስላል ። ሐዲሱን እያስተማረ ብሉዩን የሚማር ይሆናል ። አንድም ዘያወፅእ እመዝገቡ ብሉየ ። ወዘይወዲ ውስቴቱ ሐዲሰ ብሉዩን ከሣጥኑ የሚያወጣ በሣጥኑ ሐዲሱን የሚያኖር ባለጸጋን ይመስላል አእምሮን ገንዘብ የሚያደርግ ውኀደተ አእምሮን የሚያርቅ ይሆናል ።

ዘከመ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ናዝሬት።

፶፫ ወሶበ ፈጸመ እግዚእ ኢየሱስ እሉንተ ምሳሌያተ ተንሥአ እምህየ ወሖረ ሀገሮ ፤

፶፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ሁሉ በምሳሌ አስተምሮ ከፈጸመ በኋላ ከዚያ ተነሥቶ ወደ ሀገሩ ወደ ናዝሬት ሄደ ።

፶፬ ወመሀሮሙ በምኵራቦሙ

፶፬ ማር ፮ ፩ ሉቃ ፬ ፲፮ ከምኵራብ ገብቶ አስተማራቸው ።

እስከ ሶበ ይደመሙ ወይብሉ እምአይቴ እንከ ሎቱ ዝንቱ ኵሉ ጥበብ ወኃይል ፤

ይህ ሁሉ ጥበብ ኃይል ከወዴት ተገኘለት ብለው እስኪያደንቁ ድረስ ጥበብ ምሳሌ መስሎ ወኃይል ትርጓሜ ተርጕሞ ማስተማር ። አንድም ጥበብ ምሳሌ መስሎ ተርጓሚ ተርጕሞ ማስተማር ወኃይል ታምራት ማድረግ ከማን አገኘው ።

፶፭ አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለፀራቢ ። ዮሐ ፮ ፵፪ ።

፶፭ የፀራቢ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን አሉ ። በሀገራቸው ልጅ ያባቱን ሥራ ይማራል እንጅ ሌላ አይሠራምና ።

ወስማ ለእሙ ማርያም ።

እናቱስ ማርያም አይደለችምን ድኃ ማለት ነው ።

ወአኃዊሁኒ ያዕቆብ ወዮሳ ስምዖን ወይሁዳ ።

ወንድሞቹስ እነዚህ እነዚህ አይደሉምን ።

፶፮ ወአኃቲሁኒ ኵሎን ሀለዋ ኀቤነ

፶፮ እኅቶቹስ ቅኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን ። አንድም መንፈስ ቅዱስ ፊታቸውን ጸፍቶ አፋቸውን ከፍቶ ምንቀ ቢያደርግ የፀራቢ ሰማያት ወምድር የአብ ልጅ አይደለም እናቱስ እግዝእተ ብዙኃን ማርያም አይደለችም ሲያሰኛቸው ነው ።

እምአይቴ እንከ ሎቱ ዝንቱ ኵሉ ጥበብ ወኃይል ። ይህን ሁሉ ጥበብና ኃይል ከወዴት አገኘው እንዳሉ ለፈው

፶፯ ወአኃዙ ያንጐረጕሩ በእንቲአሁ ።

፶፯ ባሉ ነገር ይታወኩ ጀመር ።

ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢይትሜነን ነቢይ ዘእንበለ በሀገሩ ወበቤቱ ።

ነቢይ ከቤቱና ከሀገሩ በቀር አይነቀፍም ማለት በሀገሩ አይከበርም አላቸው ።

፶፰ ወኢገብረ በህየ ኃይለ ብዙኃ በእንተ ሕጸተ አሚኖቶሙ ።

፶፰ ስለ አለማመናቸው ብዙ ታምራት አላደረገም ።

በእንተ ሀለየ ሄድሮስ ላዕለ ኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፲ወ፬ ።

፩ ወበውእቱ መዋዕል ሰምዓ ሄሮድስ ንጉሥ ነገሮ ለእግዚእ ኢየሱስ ። ማር ፮ ፲፬ ሉቃ ፱ ፯

፩ በዚያ ወራት ሄሮድስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ነገር ሰምቶ ማለት ያደረጋውን ታምራት

የሠራውን ትሩፋት ሰምቶ ድምፀ ንገሩ ይላል አብነት የታምራቱን ዜና ሰምቶ ።

፪ ወይቤ ዝውእቱ ዮሐንስ መጥምቅ ውእቱ ተንሥአ እምውታን ።

፪ ለብላቴኖቹ ይህ ዮሐንስ መጥምቅ ነው እሱ ከሙታን ተነሥቶ ይሆናል ።
ወበእንተዝ ይትገበሩ ሎቱ ኃይላት ።
በግፍ አስገድየው ነበርና ስለዚህ ታምራት ይደረግለታል አላቸው ።

፫ እስመ ውእቱ ሄሮድስ አኀዞ ለዮሐንስ ወሞቅሖ በቤተ ሞቅሕ ማር ፮ ፡ ፲፯ ሉቃ ፫ ፡ ፲፱ ።

፫ ሄሮድስ ዮሐንስን ይዞ አስሮ አግዞት ነበርና
በእንተ ሄሮድያዳ ብእሲተ እኁሁ ፊልጶስ ።
በወንድሙ በፊልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት ።
እስመ ኪያሃ አውሰበ ።
እሷን ስለአገባ ።
፬ እስመ ይቤሎ ዮሐንስ ሎቱ ኢይከውነከ ታውስብ ብእሲተ እኁከ ፊልጶስ ።
፬ የወንድምህን የፊልጶስን ሚስት ማግባት አይገባህም ቢለው ።
፭ወእንዘ ይፈቅድ ይቅትሎ ይፈርሆሙ ለሕዝብ
፭ ሊገድለው ወዶ ሳለ ሕዝቡን ይፈራቸው ነበረ ።
እስመ ከመ ነቢይ ይሬእይዎ ለዮሐንስ ።
ዮሐንስን እንደ አባት ያፍሩታል እንደ መምህር ያከብሩታልና ።
፮ ወከዊኖ ዕለተ ልደቱ ለሄሮድስ ዘፈነት ሎቱ ወለተ ሄሮድያዳ በማእከሎሙ ።
፮ ሄሮድስ የተወለደበትን ቀን በዓል አድርጎ ሳለ ወለተ ሄሮድያዳ መጥታ በመኳንንቱ ፊት ዘፈነችለት፥ ሐተታ አሕዛብ የተወለዱበትን ቀን ያከብራሉና በዚህ ቀን ተወልደን ከዚህ ማዕርግ ደረስን ሲሉ ፣ እንድም ከጨለማ ወደ ብርሃን ከጽባብ ወደ ስፉ የወጣንበት ሲሉ ።
ወአደመቶ ለሄሮድስ ።
ሄሮድስን ደስ አሰኘችው ።
፯ ወበእንተዝ መሐለ ላቲ ከመ የሀባ ዘሰአለቶ ።
፯ ስለዚህ የለመነችውን እንዲሰጣት ማለላት።
፰ ወይእቲሰ እቅደሙት እእምሮ በኀበ እማ ።
፰ እሷ አስቀድማ ከናቷ ዘንድ ነገሩን ዐውቃው መጥታ ነበርና ታሪክ ከዕለታት ባንድ ቀን ካንች በቀር ሌላ የምወደው እንደሌለ አምላክ እስራኤል ያውቀዋል ። ነገር ግን ይኽ ነቢይ ይዘልፈናል አላት ለዚህማ ምን ቸገረህ በዓል የምታደርግበት ቀን ደርሷል ልጄ መጥታ ትዘፍንልሃለች ቸብቸቦውን እስቆርጠህ ስጣት ከዚህ በኋላ የወደድነውን እናደርጋለን አለችው ከዚህ በኋላ ስትሄድ ምን ላድርግልሽ ያለሽ እንደ ሆን ሌላ ነገር አትለምኝ ቸብቸቦውን ቈርጠህ ስጠኝ በይው ብላ መክራ ሰዳታለች ። ሂዳ ዘፈነችለት በማርቆስ እስከ መንፈቀ መንግሥቱ ይላል ፣ የመንግሥቱንም እኩሌታ ቢሆን እሰጥሻለሁ አላት ሂዳ ነገረቻት ይልቅስ የነገርሁሽን አድርጊ መንግሥቱንማ መላውን ማን ነሥቶናል አለቻት ሂዳ ፣
ወትቤሎ ሀበኒ ይእዜ ርእሶ ለዮሐንስ መጥምቅ በፃሕል ።
የዮሐንስን ራሱን አስቆርጠህ በፃሕል ስጠኝ አለችው

፱ ወተከዘ ንጉሥ በእንተ መሐላሁ ።
ስለመሐላው ማለት ከድታ አማለችኝ ብሎ አዘነ ።
ወበእንተ እለ ይረፍቁ ምስሌሁ ከሱም ጋር ሰለተቀመጡት መሐላ አፍራሽ ይሉኛል ብሎ ፣ እንድም ወበእንተ እለ ይረፍቁ ነቢየ እግዚአብሔር አስገደለ ይሉኛል ብሎ ።
ወአዘዘ የሀብዋ ።
ቆርጣችሁ ስጧት ብሎ አዘዘ ።

፲ ወፈነዎ መስተራትዓተ ሐራ ።

፲ ጭፍራውን የሚሠሩ የሚቀጡ ባለወጎችን ላከ ቤተ እንግዳ ቤተ እይጽ ሲቃይ ቀራጭ እንዳለ ።
ወመተሩ ርእሶ ለዮሐንስ በቤተ ሞቅሕ ።
በግዞት ቤት ሳለ የዮሐንስን ራስ ቀረጡ ።

፲፩ ወአምጽኡ ርእሶ በፃሕል ወወሀብዋ ለይእቲ ወለት ።

፲፩ በፃሕል አምጥተው ለብላቴናዪቱ ሰጧት ። ሐተታ ለጊዜው እስራኤል ደም ይጸየፋሉ ፍጻሜው ግን የከበረ የዮሐንስ ራስ በዚች በርኩስት እጅ እንዳትያዝ ነው ።

ወይእቲ ወሀበት ለእማ ፣ እሷም ወስዳ ለናቷ ሰጠች ግዳይ ጣለች ። ሐተታ ትስፋም ትፈትልም ነበር ቢሉ ንጉሥ ንግሥት ስትዘልፍ አታፍር የነበረች እንደበት ታተመች ብላ በያዘችው ግልጽልጽ አደረገችው ወተሰፍሐት ይእቲ ርእሰ ወሠጠቀት ዓረፍተ ቤት እንዲል ፣ ሁለት ክንፍ አውጥታ ግንቡን ሠጥቃ ወጥታ ጌታ በደብረ ዘይት ሲያስተምር ሂዳ ሰገደችለት ። ባለሽበት ተወሰንሽ አስተምሪ አላት ። ዐሥራ አምስት ዓመት አስተምራ በብሔረ ዓረቢያ ዐርፋለች ነጋድያን ሲያልፉ እንደ ዕንቍ ስታበራ አይተው የመምራችሁ ራስ ከዚያ ወድቃለች ብለው ለደቀ መዛሙርቱ ነገሯቸው ወስደው ቀብረዋታል ።
እሷስ እንደምን ሁናለች ቢሉ እናትና ልጁ ዘፈን እናደርሳለን ብለው ሲሄዱ እናቲቱን ምድር ተከፍቶ ዋጣት ልጂቱ እናቴን ብላ እጅዋን ይዛ ቀርታለች ። ከዚህ በኋላ ሄሮድስን ኢይደልወከ ታውስብ ብእሲተ እኁከ ፊልጶስ አለችው ቀድሞ ያልሆነ ሥራ ታሠራ በኋላ ምሥጢር ታወጣንሳ በሰይፍ በላት ብሎ በሰይፍ አስመትቷታል ። ገድሉ እንበሪ ዋጣት ይላልሳ ቢሉ ሁሉም ተደርጎባታል የሚሰይፍበት ቦታ ከባ

ሐር ፥ አጠገብ ነው በሰይፍ መታት ደም ተከሉዋት ወርዳ ከባሕር ወደቀች እንበሬ ተቀብሉ ዋጣት ። እንድም ገና ሳይቀጣት ፥ የታዘዘ እንበሬ ያዛት የንጉሥ ትእዛዝ አይቀርምና በሰይፍ መትቷት ሩቢል ተቀብሎ ውጧታል ። አንድም እናትና ልጁ ሄደው ሄሮድስን ኢይደልወከ ታውስብ ብእሴቶ እኁከ ፊልጶስ እሴቶ ቀድሞ ያልሆነ ሥራ ያሠራ ኋላ ምሥጢር ያወጣ ብሎ አስከንገላቸው እልቀብር መን ኢሰንድቀባቸዋል ። አንድም እናትና ልጁ ዘፈን እና ድሳለን ብለው ሲሄዱ እናቲቱን ምድር ተከፍቶ ዋጣት አንድ ሰው እጅዋን ይዞ ቀረ ልጂቱ ሄዳ ሄሮድስን ኢይደልወከ ታውስብ ብእሲተ እኁከ ፊልጶስ አለችው ቀድሞ ያልሆነ ሥራ ታሠራ ኋላ ምሥጢር ታወጣ ንሳ በሰይፍ በላት ብሎ በሰይፍ አስመትቷታል ። ያ ሰው እናቷም እንጂ እንዴህ ሁና ሞተች እሰ በምን ፀውቀህ አሉት እጅዋን አሳይቷል ። እቡስ እንደምን ሁነዋል ቢሉ አወጣ የሚባል አግች እሰው ዘማትን እየሰበሰበ ልጇን ያሰቀናታል ሆነ ብሎ አገር መታ ቁማር ይህን ሰምቶ ያስደፈረኝ እሱ እኝሺ ነው ብሎ አስጠርቶ ወስዶ አጋዘው ከዚያ እእምሮውን አጥቶ የገዛ አካሉን እየነጨ እየበላ ሸቶ ተልቶ እብዘ ፈንድቶሙ ብሎ ደርቆ ተበላሽቶ ሙቷል ። ወሞቶ ጻድቅ ይኳንን ረሢዓነ ያለው ሊደርሰ ሊፈጸም ።

፲፪ ወመጽኡ አርዳኢሁ ወነሥኡ በድኖ ወቀበርዎ ።

፲፪ ደቀ መዛሙርቱ ፀድኑን ወሰደው ቀበሩት ልቡ ሰጻድቅ ውኩል ኪመ አንበሳ እንዲል ርሱን ያገኘ ያገኘናል ሳይሉ ወመጺኦሙ ዜነውዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
መጥተው የዮሐንስን ሞት ለጌታ ነገሩት ።

በእንተ ቀዳሚት አብዝኖተ ኅብስት ።

፲፫ ወሰሚዖ እግዚእ ኢየሱስ ተግኅሠ እምህየ በሐመር ውስተ ገዳም እንተ ባሕቲቱ ።
ማር ፮ ፡ ፴፩ ። ሉቃ ፱ ፡ ፲ ፥ ዮሐ ፮ ፡ ፩ ።

፲፫ ጌታም የዮሐንስን ሞት ሰምቶ ከባሕር በመርከብ ተጭኖ ወደ ገዳም ሄደ ። ሐቀታ እርድእተ ዮሐንስ ኀዘንተኞች ናቸውና ለማሳረፍ ፥ አንድም ሰብእ ሁለቱ እርድዕት መጥተው እጋንንት ገረሩ ለነ ብለውታል ነገሩ እንደምን ነው ስማለት ።
ወሰሚዖሙ ሕዝብ ተለውዎ በእግር እምበሐውርት ሕዝቡ መሄዱን ሰምተው ከሀገሩ ተወጣጥተው የብሱን በእግር ተከተሉት ።

፲፬ ወወፂኦ ርእየ ብዙኃነ እሕዛብ ፤

፲፬ በወጣም ጊዜ ብዙ ሰው አየ ወምሀርሙ ። አዘነላቸው ወእሐየወ ድውያኒሆሙ ፡ ድውያኑን አዳነ ።

፲፭ ወምሴተ ከዊና ቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ ወይቤልዎ ገዳም ውእቱ ብሔር ።

፲፭ ሲመሽ በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው እዩት ምድሩ በዳ ነው ።
ወሰዓትኒ ኃለፈ ፋትሐሙ ለሕዝብ ።
ጊዜውም መሸቷል ሕዝቡን አሰናብታቸው አሉት ከመ ይሑሩ ውስተ አህጉር ወይሳየጡ ለርእሰሙ መብልዓ ወደ ሀገር ገብተው ምግባቸውን ይገዙ ዘንድ ፥ ሐተታ በቤተሰብ ልማድ እሰን እሰን ባዮች ናቸውና እሁን ዝም ብለን ኋላ ለዚህ ሁሉ ሰው ምግብ አቅርቡ ቢለን ከወዴት እናመጣለን ብለው

፲፮ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አኮ መፍትው ይሑሩ ርኅቀ ሆሙ ።

፲፮ እንዳ ተራቡ ሲሄዱ አይገባም አላቸው እላ አንትሙ ሁብዎሙ ዘይበልዑ ።
የሚበሉትን እናንተ ስጡቸው እንጂ ።

፲፯ ወይቤልዎ አልብነ ዝየ ዘእንበለ ኃምስ ኅብስት ወ፪ቱ ዓሣ

፲፯ ከዚህ ከሁለት ዓሣና ካምስት እንጀራ በቀር ሌላ የሰንም አሉት ።

፲፰ ወይቤሎሙ አምጽእዎን ሊተ ዝየ ።

፲፰ ይህስ ካሰ ወዲህ አምጡልኝ አላቸው ።

፲፱ ወአዘዞሙ ለሰብእ ይርፍቁ ዲበ ሣዕር ።

፲፱ ከመሬቱ ተቀመጡ አላቸው ። ወነሥአ ውእተ ኃምስ ኅብስተ ወ፪ኤ ዓሣ ወነጸረ ሰማየ ። ሁለቱን ዓሣ አምስቱን እንጀራ ይዞ ወደ ሰማይ አየ ። ሐቲታ ይህን ኅብስት የማበረክትበት ሥልጣን ካንተ ጋራ አንድ ነው ሲል አንድም ታምራት ይደረግልን ባላችሁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር አመልክቱ ለማለት አብነት ለመሆን ። ባረከ ነመበ ቀረሰ ፥ ወፈተተ ፤ አጢቃቀነ ። ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ። ለደቀ መዛሙርቱ ሰጡ ብሎ ሰጣቸው ።
ወአርዳኢሁኒ አቅረቡ ለሕዝብ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ አቀረቡ በሱም እጅ በሐዋርያትም እጅ ሳለ ይበረከት ነበር በረከት መንፈሳዊ እሰከ ምጽአት እንዳያቋርጥ ያጢይቃል ።

፳ ወበልዑ ኵሎሙ ወጸግቡ ።

፳ ሁሉም በልተው ጸገቡ ።
ወአግኃሡ ዘተርፈ ፍተታተ ። የተረፈውን አነሡ ወመልዓ ዐሥርተ ወ፪ተ መዛርዓ ምሉእ ።
መሳይምት እክፋሬ እስፈሬዳተ ይላል ጋዘና መሶብ ቅርጫት ማለት ነው ።

፳፩ ወእለሰ በልዑ የአክሉ ፶፻ ዕደው ዘእንበለ አንስት ወደቅ ።

፳፩ የበሉት ሰዎች ከሴቶችና ከሕፃናት በቀር ፭ሺህ ያህል ይሆናሉ በሀገራቸው ሴትና ወንድ አቀላቅሎ መቍጠር የለምና ዘእንበለ አንስት አለ ፥ ልጆችም አይበሉምና ፥እንድም ሴቶች ወንድ ሲያያቸው

ያፍራሉና ሕፃናትም ከሚበሉት የሚያበላሹት ይበዛልና ፲፪ ማንግታቸው ባሥራ ሁለቱ ሥዩማን ባሥራ ሁለቱ ከዋክብት ምሳሌ ፣ በልተውሰት የተረፈው በዘመነ ሐዲስ የተገለጸ ምሥጢር ነው ካራቱ ባሕርያት ካምስተኛ ባሕርየ ነፍስ የተፈጠረ ሰው የሚቻለውን ያህል ነሥቶበት የቀረው በልበ ሐዋርያት እንደ ቀረ ያጠይቃል ። አምስቱ ያምስቱ አዕማደ ምሥጢር ሁለቱ ዓሣ የፍቅረ ቢጽና የፍቅረ እግዚአብሔር አንድም የሥጋው የደሙ ምሳሌ ፣ የተረፈውንም ከማርያም መግደላዊት ቤት አትረውት በዘመነ ደዌ ለፈውስ በዘመነ ቀጠና ለበረከት ይወስዱት ነበር ሲመሽ ያደረገው ጪት ያላደረገው ስለምን ቢሉ ጪት አድርጎት ቢሆን ምሳቸውን የበሉ ምሳትንን በልተን ያልበሉ የበላነው ሳይሰማማን ብንበላው በረከተ እንጂ እንዳይሉ ሁሉም በሚሹበት ጊዜ አደረገው ምሥጢሩ ግን በፍጻሜ ዘመን መንፈሳዊ ምግብ እመግባችኋለሁ ሲል ነው በገዳም ያደረገው ስለምን ቢሉ ለጊዜው ከመንደር አጠገብ አድርጎት ቢሆን ፈጣን ፈጣን ደቀ መዛሙርት እሉትና ከዚያም ከዚያም እያመጡ በላይ በላዩ እየጨመሩበት በረከተ እንዳይሉ ፣ ፍጻሜው ግን እሥራኤል በገዳም ፵ ዘመን መና የመገብሁ እኔ ነኝ ሲል አንድም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በመንግሥተ ሰማያት መንፈሳዊ ምግብ እመግባችኋለሁ ሲል ፣ በመሸ ያደረገው ስለምን ቢሉ ለጊዜው ለልብሳችን በንጠነቀቅ ባንበላው በረከተ እንጂ እንዳይሉ ፣ ምሥጢሩ ግን በምቹ ቦታ በመንግሥተ ሰማይ እኖራችኋለሁ ሲል ፣ በወኃ አጠገብ ያደረገው ስለምን ቢሉ ለጊዜው እጃችንን ባንታጠብ ተጸይፈን ባንበላው በረከተ እንጂ እንዳይሉ ፣ ምሥጢሩ ግን በጥምቀት በሚገኝ ክብር አከብራችኋለሁ ሲል ።

ዘከመ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ መልዕልተ ማይ ።

፳፪ ወአገበሮሙ ሶቤሃ ለአርዳኢሁ ከመ ይዕርጉ ውስተ ሐመር ወይቅድምዎ ኀበ ማዕዶተ ባሕር እስከ ሶበ ይፌንዎሙ ለአሕዛብ ። ማር ፮ ፡ ፵፭ ።

፳፪ ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ቢራቡ ያመሳል ቢታመሙ ይፈውሳል ቢሞቱ ያሥነሣል እንዲህ ያለውን ቢያነግሡት ምን ይብሳል ነገር ግን ማን ይይዝልናል ብለዋል ሐዋርያት እለን እለን ባዮች ናቸውና እኛ እያለን እኛ እንይዝላችኋለን ብለዋቸዋል፤ ሕዝቡን እስኪያሰናብት ድረስ በመርከብ ተጭነው ባሕሩን ተሻግረው ይቆዩት ዘንድ ተሻግራችሁ ቆዩኝ አላቸው ። አንድም ሲይዙት ወደው ፈርተው ቆመዋል ዐውቆባቸው ሂዱ ብላችሁ አላቸው ።

፳፫ ወእምዝ ፈቲሖ አሕዛበ ዐርገ ውስተ ደብር እንተ ባሕቲቱ ይጸሊ ። ዮሐ ፮ ፡ ፲፭ ።

፳፫ ከዚህ በኋላ ሕዝቡን አሰናብቶ ለብቻው ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ ። ሐተታ ሰውም እያንግሡኝ ልዑለ ባሕርይ ነኝ ሲል ይፀሊ ግለቱ ታምራት ተደረገልን ብላችሁ ጸሎታችሁን አትተው ለማለት አብነት ለመሆን ።
ወምሴተ ኮነ ባሕቲቱ ሀሎ ህየ ሲመሽ ብቻውን ከዚያ ነበር ።

፳፬ ወሐመርሰ ናሁ ማእከለ ባሕር ሀሎ ።

፳፬ መርከቡ ግን እነሆ ከባሕር መካከል ነበር። ወርኅቅ እምሐይቅ መጠነ እሥራ ወ፭ቱ ምዕራፍ ከወደቡ ሃያ አምስት ምዕራፍ ያህል ርቆ ነበር ።
ወይትሀወክ እሞገድ ።
ከማዕበሉ የተነሣ ይናወጽ ነበር እስመ እምቅድሜሁ ውእቱ ነፋስ ።
ነፋስ ከወደፊቱ ተነሥቶ ነበርና ።

፳፭ ወበራብዕት ሰዓተ ሌሊት መጽአ ኀቤሆሙ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ የሐውር ዲበ ባሕር ።

፳፭ ባራተኛው ሰዓተ ሌሊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕር ላይ እየሄደ መጣ ። ሐተታ ፣ ቀዳማይ አካች ካልዓይ አካች ሣልሳይ አካች ራብዓይ አካች አለና ፣ ምሥጢሩ ግን በአራተኛው ክፍለ ዘመን ጌታ ሰው መሆኑን ያጠይቃል ።

፳፮ ወሶበ ርእይዎ አርዳኢሁ እንዘ የሐውር ዲበ ባሕር ደንገፁ ወተሀውኩ እንዘ ይብሉ ምትሐት ውእቱ ።

፳፮ ደቀ መዛሙርቱ በባሕር ሲሄድ ባዩት ጊዜ ምትሐት መስሏቸው ፈሩ ደነገጡ ። ሐተታ ፣ ከሄሮድስ ከተማ ያስወጣነው ሰይጣን በየብስ መጣላት ባይሆንለት ነፋስ አምጥቶ ማዕበል ሞገድ አስነሥቶ ሊያሰጥመን መጣ ብለው ። ወእምግርማሁ አውየው እሱን ከመፍራታቸው የተነሣ አሰምተው ተናገሩ ።

፳፯ ወበጊዜሃ ተናገሮሙ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይብል አነ ውእቱ ወኢትፍርሁ ።

፳፯ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጥኖ እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው ።

፳፰ ወአውሥአ ጴጥሮስ ወይቤሎ እመሰ አንተሁ እግዚኦ አዝዘኒ እምጻእ ኀቤከ እንተ ዲበ ማይ

፳፰ ጴጥሮስ መልሶ አቤቱ አንተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወዳንተ እመጣ ዘንድ እዘዘኝ አለው ።

፳፱ ወይቤሎ ነዓ ።

፳፱ ና አለው ።
ወወሪዶ ጴጥሮስ እምዲበ ሐመር ሖረ ዲበ ማይ ይብጻሕ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጴጥሮስ ወደ ጌታ ሊደርስ ከመርከብ ወርዶ በውኃው ላይ ሄደ ሃይማኖቱ ውኃውን እንደ ፍንጃል አጽንቶለት ።

፴ ወሶበ ርእየ ነፋሰ ኃያለ ።

፴ ጽኑ ነፋስ ሲነፍስ ባየ ጊዜ ፈራ ማለት ሃይማኖቱን ሰቀቀ ወአኃዘ ይሰጥም ።
ውኃውም ጽንዑን ለቀቀው ይሰጥም ጀመር ።

ወአውየወ ሶቤሃ እንዘ ይብል እግዚኦ አድኅነኒ ። ያን ጊዜ አቤቱ አድነኝ ብሎ አሰምቶ ተናገረ ።

፴፩ ወሶቤሃ ሰፍሐ እዴሁ እግዚእ ኢየሱስ ወአኀዞ ።

፴፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያን ጊዜ እጁን ዘርግቶ አወጣው ።
ወይቤሎ ዕውኁደ ሃይማኖት ለምንት ናፈቅ ፤ አንተ ሃይማኖተ የሌለህ ለምን ትጠራጠራለህ ከሱ ጋራ ሳለሁ ጥፋት አያገኝኝም በሱ ስም አጸና ዋለሁ አትልም አለው ። ሐተታ ሃይማኖቱ ፍጹም ቢሆን የፍጹም ሥራ ሠራለት ሃይማኖቱ ወጣኒ ቢሆን የወጣኒ ሥራ ሠራበት ። እንደ ሦስቱ መነኩሳት ወደ አባ እንጦንስ ሲሄዱ አንዱ ከመንገድ ሞተ አንዱ ደከሞ ቀረ አንዱን እድ ብርሀት እየመራች ከሱ ዘንድ አድርሳዋለች ። አባ አሞን ይባላል ያንን ሰው ሰዶ አስመጥቶታል ፤ ይ የወጣኒ ይህ የፍጹም ፤

፴፪ ወአሪጎ ውስተ ሐመር ውእተ ጊዜ ኅደገ ነፋስ ወኮነ ዛኅነ ።

፴፪ ወደ መርከብ በወጣ ጊዜ ነፋስ ጸጥ አለ ።

፴፫ ወእለሰ ውስተ ሐመር ሰገዱ ሎቱ እንዘ ይብሉ አማን ወልደ እግዚአብሔር አንተ ።

፴፫ በመርከብ ያሉት በውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት ፤ አንድም ትስብእቱን በማመን ያሉ በውነት የአብ የባሕርይ ልጁ ነህ ብለው ሰገዱለት ።

ዘከመ ዓደወ ውስተ ጌንሴሬጥ ፤

፴፬ ወዓደዉ በጽሑ ምድረ ጌንሴሬጥ ማር፥ ፮ ፥ ፶፫ ።

፴፬ ባሕሩን ተሻግረው ጌንሴሬጥ ደረሱ ። ጌንሴሬጥ ባሕሩ ምድር ወደቡ ነው ።

፴፭ ወአእመርዎ ሰብአ ውእቱ ብሔር ።

፴፭ የዚያ አገር ሰዎች አይተው አወቁት ።
ወፈነው ኀበ ኵሉ አድያም ።
ወደ ሀገሩ ሁሉ ላኩ ። ድውይ ያለህ ምዘዝ አሉ ።
ወአምጽኡ ሎቱ ኵሎ ሕሙማነ ።
ሕሙማኑን ሁሉ አመጡለት ።

፴፮ ወአስተብቍዕዎ ከመ ይግሥሡ ዘፈረ ልብሱ ።

፴፮ የልብሱን ዘርፍ ይዳሥሡ ዘንድ ማለዱት ።
እስመ ኵሎሙ እለ ገሠሥዎ የሐይዉ ።
የልብሱን ዘርፍ የዳሰሱ ሁሉ ይድኑ ነበርና ።

በእንተ ፈሪሳውያን ወሥርዓቶሙ ።

ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወእምዝ መጽኡ እምኢየሩሳሌም ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ማር ፯ ፥ ፩ ።

፩ ዝ ሲናገረው የመጣ ነው ። ከዚህ በኋላ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ከኢየሩሳሌም ወደ ጌታ መጡ ።

፪ እንዘ ይብሉ ለምንት ይትዓደዉ አርዳኢከ ሥርዓተ ረበናት ወትእዛዞሙ ለሊቃነ ካህናት ።

፪ ደቀ መዛሙርትህ የረበናትን ሥርዓት የሊቃነ ካህናትን ትእዛዝ ለምን ይተላለፋሉ አሉት ። እስመ ኢይትሐፀቡ እደዊሆሙ ሶበ ኅብስተ ይበልዑ እንጀራ በሚበሉበት ጊዜ እጃቸውን አይታጠቡም ነበርና ይላል ጸሐፊው ። ስእመ ብሕቁ ኢተሐጽቡ ይላል በማርቆስ ።
እነሱ መሳልሰው ደም እስኪሰርበው እስኪመለጥ ካልታጠቡ አይበሉም ነበር ።

፫ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ለምንት አንትሙኒ ትትዓደዉ ትእዛዘ እግዚአብሔር በእንተ ሥርዓትክሙ ።

፫ እናንተስ የናንተን ሥራት ለማጽናት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለምን ታፈርሳላችሁ አላቸው

፬ ወእግዚአብሔር ይቤ አክብር አባከ ወእመከ ዘፀ ፡ ፳፡፲፪ ። ዘዳ ፭፡፲፮ ። ኤፌ. ፮፡፪ ። ዘፀ ፳ ፡ ፩፲፯, ዘሌ ፳ ፡ ፱ ምሳ ፳ ፡ ፳ ።

፬ እግዚአብሔርስ እናት አባትህን አክብር ማለት እርዳ ብሏል ።
ወዘእሕሠመ ቃለ ላዕለ አቡሁ ወእሙ ሞተ ለይሙት ባባቱና በናቱ ክፉ ነገር የሚናገር ማለት አባት እናቱን አልረዳም ያለ ሰው ፈጽሞ ይሙት ብሏል ።

፭ ወአንትሙሰ ትብልዎ ዘይቤሎ ለአቡሁ ወለእሙ ሀብተ ቍርባን ዘረባኅከ እምኔየ ።

፭ እናንተ ግን ካኔ ይልቅ ይረባኛል ይጠቅመኛል ያልከው ይርዳህ ያጽባሕ ። አንድም ዘረበሐከ ዘበቍዓከ ይላል ። እኔን ከመውለድህ የተነሣ የበላኸው መሥዋዕት የረባህ የጠቀመህ ነው በለው ትሉታላችሁ ። ሐተታ አዕሩገ እሥራኤል የወለዱት የሚበሉት ያልወለዱት የሚበሉት መሥዕት አለና ፤ አንድም ዘረባሕኩከ ዘበቋዕኩከ ይላል ። እኔን ለቤተ እግዚአብሔር ከመስጠትህ የተነሣ እሰጥሃለሁ ያልኩህ ገንዘብ የቤተ እግዚአብሔር ነው በለው ብላችሁ ላባትና ለናቱ የሚመልሰውን ምላሽ ትነግሩታላችሁ ። ጌታ ሙሴን የግብጻውያንን በኵር አጥፍቼ አውጥቻችኋለሁና በኵር ለኔ ይገባል በኵሩን ለይልኝ አለው ቢያስቈጥር ሁለት እልፍ ከሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ሆኑ ። ሌዋውያንን ቈጠራቸው አለው ፤ ሁለት እልፍ ከሁለት ሺህ ሆኑ ፤ በሁለት እልፍ ከሁለት ሺህ በኵር እኒህን ተቀብ ያለሁ የሁለት መቶ ሰባ ሦስቱን ዋጋ አምስት አምስት ቀመት እየተቀበልህ ከቤተ እግዚአብሔር አግባ ገንዘብ ያለው ገንዘብ እየሰጠ ልጁን ይውሰድ ፤ ገንዘብ የሌለው ልጁን ይስጥ ብሎታል ገንዘብ ያለው እየሰጠ ልጁን አስቀርቷል ገንዘብ የሌለው ልጁን ሰጥቷል ፤ የመቶው አምስት መቶ የመቶው አምስት መቶ የስሳው ሦስት መቶ ያሥሩ አምሳ የሦስቱ አስራ

አምስት ሽህ ከምስት መቶ ሰላ አምስት ይሆናል ። ከዚህ በኋላ አባት እየደከመ ገንዘቡ እያለቀበት ልጅ ገንዘብ እያገኘ ይሄዳል ምንስ ለቤተ እግዚአብሔር ብሰጠው ልጄ አይደስምን ርዳኝ ልበለው ብሎ ይሄዳል እንዲህ ብለህ መልሰለት ብለው ተንኰል ያስተምሩታልና ።

፭ ዘብሂል ኢያከብር አባሁ ወእሞ፤

፮ እንዲህ ማለት እናት አባቱን አይርዳ ማለት ነው ።

ወሠዓርክሙ ቃሎ ለእግዚአብሔር በእንተ ሥርዓትክሙ ።

የናንተን ሥርዓት ለማጽናት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፈረሳችሁ ።

፯ አ መደልዋን ሠናየ ተነበየ ኢሳይያስ ላዕሌክሙ ።

፯ እናንት ግብዞች እሙን ሲል ነው ኢሳይያስ በናንተ እውነት ነገርን ተናገረባችኋል ።

፰ እንዘ ይብል ዝ ሕዝብ በከናፍሪሆሙ ያከብሩኒ ። ኢሳ ፳፱ ፣ ፲፫ ማር ፯ ፣ ፮ ።

፰ እኒህ ሕዝብ በአፋቸው እናከብርሃለን ይሉኛል ማለት እናምንብሃለን ይሉኛል ።
ወበልቦሙሰ ነዋኀ ይርኅቁ እምኔየ ።
በልቡናቸው ግን አስረዝመው ይርቃሉ ማለት ዕሩቅ ብእሲ ይሉኛል ።

፱ ወከንቶ ያመልኩኒ ።

፱ በሐሰት ያመልኩኛል ።
እንዘ ይሜህሩ ትምህርተ ሥርዓታተ ሰብእ ።
የሰውን ሥርዓት እያስተማሩ ማለት ሰው ሠራሽ ትምርት እያስተማሩ ።

፲ ወጸውዖሙ ለሕዝብ ወይቤሎሙ ስምዑ ወለብዉ ከመ አኮ ዘይበውእ ውስተ አፍ ዘያረኩሶ ለሰብእ ። ማር ፡ ፯ ፡ ፲፬ ።

፲ ሕዝቡን ጠርቶ ሰውን የሚጎዳው ባፍ የሚገባው እንዳይደለ ስሙ ዕወቁ አላቸው ።

፲፩ አላ ዘይወፅእ እምውስተ አፍ ውእቱ ያረኩሶ ለሰብእ ።

፲፩ ካፍ የሚወጣው እሱ ይጎዳዋል እንጂ ።

፲፪ ወእምዝ ቀረቡ አርዳኢሁ ይቤልዎ ኢተአምርሁ ከመ ፈሪሳውያን ሰሚዖሙ ቃለከ አንጐርጐሩ ።

፲፪ ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው ፈሪሳውያን ትምህርትህን ሰምተው እንዳዘኑ አታውቅምን አሉት ። እንደዚህማ ከሆነ ጅብም ቀበሮም ቢበሉ አይጎዳማ ብለው ነው ሐዋርያት በነገሩ እያሉበት ፈሪሳውያንን ጥግ አድርገው ይጠይቁታል ።

፲፫ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ኵላ ተክል እንተ ኢተከላ አቡየ ሰማያዊ ትሴረው ዮሐ፣ ፲፭ ፣ ፪ ።

፲፫ ሰማያዊ አባቴ ያልሠራት ሥራ ሁሉ ታልፋለች ትሾር ትለፍ አላቸው ።

፲፬ ኅድግዎሙ እስመ ዕውራን እሙንቱ እምሀርተ ዕውራን ። እምርሀት እምሀርት ይላል ።

፲፬ የዕውራን አእምሮ መሮች መምሮች ናቸውና ተዋቸው አለዕውር ዕውረ ለእመ መርሀ ፪ሆሙ ይወድቁ ውስተ ግብ ። ዕውር ዕውሩን ቢመራው ሁለቱም ከጉድጓድ ይወድቃሉ ዕውር ዕውርን ቢከተል ተያይዘው ገደል እንዲሉ ።

፲፭ ወአውሥአ ጴጥሮስ ወይቤሎ ንግረነ ዘንቱ ምሳሌ ማር ፡ ፯ ፡ ፲፯ ።

፲፭ ጴጥሮስ መሰለ ይህን ነገር ተርጉመህ ገልጸህ ንገረን አለው ሃናክ ወመጽኡ ዲቤየ ሠለስቱ ምሳሌያት ካለው አንዱን ነገር እንዳለው ።

፲፮ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስን ዓዲሁ አንትሙኒ ኢለበውክሙኑ ዘንተ ።

፲፮ ጌታም እናንተም ገና ይህን አላወቃችሁትም አላቸው ።

፲፯ ኢተአምሩኑ ከመ ኵሉ ዘይበውእ ውስተ አፍ ውስተ ከርሥ ይትገመር ፤

፲፯ ባፍ የሚገባው ሁሉ ሆድ እንዲወስን አታውቁምን ወጽመ ይትከዐው ።
ጥቂት ቆይቶም እትዲፈስ ወጽኡ ይትከዓው ይላል በማርቆስ ። እሠር እሠሩ እንዲፈስ ሐተታ የበላነውን የጠጣነውን መሬት ይሸከማል ውኃ ያረጥባል ። እሳት እንደ ገና ያበስላል ነፋስ አረቄ አረቄውን ወደ ላይ ይዞ ይወጣል የሰው አሥራው ፫ ፻፷፭ ነው ፯ቱ ለስሳው ስሳው ለስድስት መቶው ያቀብላሉ በዚህ ጊዜ አሠር አሠሩ ቁልቁል ይወርዳልና ።

፲፰ ወዘሰ ይወፅእ እምውስተ አፍ እምልብ ይወፅእ ።

፲፰ በአፍ የሚያወጣው ግን ከልብ ይወጣል ወውእቱ ያረኩሶ ለሰብእ ። ይህ ሰውን ይጎዳዋል ሰውን የሚጎዳው ይህ ነው ።

፲፱ እስመ እምውስተ ልብ ይወፅእ ሕሊና እኩይ

፲፱ ከልብ ክፉ አሳብ ይነቃልና ዘውእቱ ቀቲል እኩይ ያለውን ይተረትራል ያውም ነፍስ መግደል ነው ወዝሙት ፣ ዝሙት ነው ስርቅ ፤ መስረቅ ፤ ስምዕ በሐሰት ። በሐሰት መመስከር ነው ።

፳ ወፅርፈት

፳ ስድብ ነው ። እሉኬ ዘያረኩስዎ ለሰብእ ሰውን የሚጎዱት እሊህ ናቸው እሊህ ሰውን ይጐዱታል ። ወዘእንበለ ተሐፅቦ እደው በሊዕ ኢያረኩሶ ለሰብእ ።
እጅ ሳይታጠቡ መብላትስ ሰውን አይጎዳውም በይውም መሬት ተበይውም መሬት ምን ይጎዳል ።

፳፩ ወወፂአ እግዚእ ኢየሱስ እምህየ ተግኅሠ ውስተ ደወለ ጢሮስ ወሲዶና ።

፳፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና አውራጃ ገባ ።

በእንተ ከነናዊት ።

፳፪ ወናሁ መጽአት ብእሲት ከነናዊት እም ውእቱ አድዋል ፤

፳፪ ማር ፣ ፯፣፳፭ ። ከነናዊት ከነዓናዊት ይላል ከነናዊት ቢል የከናኔዎን ወገን ከነዓናዊት ቢል የከነዓን ወገን የምትሆን ሴት ከዚያ አውራጃ መጣች ።
እንዘ ትጸርኅ ወትብል መሀረኒ ወልደ ዳዊት ።
ወልደ ዳዊት አቤቱ እዘንልኝ እያለች እየጮኸች ።
እስመ ለወለትየ እኩይ ጋኔን አኃዞ ።
ልጄን ቢስ ጋኔን አድሮባታልና ፣ ወየዓብዳ አእምሮዋን ያሳጣታልና ፤

፳፫ ወኢያውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ቃለ ፤
፳፫ ጌታም ነገር አልመለሰላትም ወቀረቦሙ አርዳኢሁ አስተብቍዕዎ እንዘ ይብሉ ፈንዋ ለዛቲ ብእሲት ።
ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው ይህቺን ሴት አሰናብታት ብለው ማለዱት ።
እስመ ትጸርሕ በድኅሬነ። በኋላ በኋላችን ትጮሃለችና ሐተታ ፤ ትምህርት ታስፈታለች ብለው ። አንድም ወይ ተናግረው እያስደርጉ ወይ እያሰናብቱ ትላለች ብለው ብታሳዝናቸው ።
፳፬ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ኢተፈኖኩ ዘእንበለ ኀበ አባግዕ ዘተኃጕላ ለቤተ እስራኤል፣ ማቴ ፲ ፣ ፮ ።
፳፬ ትምርት መምህር አጥተው የተጎዱ እስራኤልን ሳስተምር ሰው ሁኘለሁ እንጂ ፣ ያለዚያ ሰው አልሆንኩም ብሎ መለሰላቸው ።
፳፭ ወቀሪባ ሰገደት ሎቱ ። ማር ፯ ቍ. ፳፭ ።
፳፭ ቀርባ ሰገደችለት እንዘ ትብል እግዚኦየ ርድአኒ አቤቱ ጌታዬ እዘንልኝ ብላ ።
፳፮ ወአውሥአ ወይቤላ ኢኮነ ሠናየ ነሢአ ኅብስተ ውሉድ ወወሂብ ለከለባት ።
፳፮ የልጆችን ዳቦ ለውሻ መስጠት አይገባም ማለት ለእስራኤል የማደርገውን ታምራት ለአሕዛብ አላደርገውም አላት ።
፳፯ ወትቤሎ እወ እግዚእ ።
፳፯ አቤቱ አዎን ውሻ ነኝ አለችው ከለባትኒ ን ይበልዑ እምፍርፋራት ዘይወድቅ እማዕደ አጋዕዝቲሆሙ ።
ውሾችም እንጂ ውሾችም እኮን ከጌታቸው ማዕድ የወደቀ ፍርፋሪን ይመገባሉ ። እንደዚህስ ሁሉ ለእስራኤል ደጋጉን ታምራት ብታደርግላቸው ለኔ ጥቃቅኑን ታምራት አታደርግልኝም አለችው ።
፳፰ ወእምዝ አውሥአ ።
፳፰ ከዚህ በኋላ መለሰ ።
ወይቤላ ብእሲቶ ዓቢይ ሃይማኖትኪ ።
አንቺ ሆይ ሃይማኖትሽ ታላቅ ነው ማለት ፍጹም ነው ።

ይኩንኪ በከመ ተአመንኪ ።
እንዳመንሽ ይደረግልሽ አላት ሐተታ ሦስት ነገር አግኝቶላታል ሃይማኖት ትሕትና ጥበብ ፣ ሃይ ማኖት ያድንልኛል ብሎ መምጣት ። ትሕትና በውሻ ቢመስላት አዎን ውሻ ነኝ ማለት ጥበብ መስሎ ቢነግራት መስሎ መናገር ነው ።
ወሐይወት ወለታ እምእይቲ ጊዜ ።
በዚያን ጊዜ ልጅዋ ዳነች ።

ዘከመ ተፈወሱ ካልአን ሕሙማን ።

፳፱ ወኃሊፎ እግዚእ ኢየሱስ እምህየ በጽሐ ኀበ ሐይቀ ባሕር ዘገሊላ ፤

፳፱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚያ አልፎ ከገሊላ ባሕር ወደብ ደረሰ ።
ወዓሪጎ ደብረ ነበረ ህየ ፤
ከዚያ ከተራራ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ ።
፴ ወቀርቡ ኀቤሁ አሕዛብ ብዙኃን እንዘቦ ምስሌሆሙ ሐንካሳን ወጽውራን ወጽሙማን ወዕውሳን ። ኢሳ ፣ ፴፭ ፣ ፭ ።
፴ ብዙ ሰዎች ዕውራንን ሐንካሳንን ደንቆሮዎችን ልምሾ የሆኑትንም ይዘው መጡ ።
ወባዕዳነሂ ብዙኃነ ድውያነ ሌሎችን ብዙ ድውያንን አመጡ ።
ወገደፍዎሙ ታኅተ እገሪሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ። ከእግሩ አፈሰሷቸው ፣ ወፈወሶሙ ፤ አዳናቸው ።
፴፩ እስከ ሶበ አሕዛብ ያነክሩ እንዘ ይሬእዩ ከመ በሐማን ይትናገሩ ።
፴፩ በሐማን ሥጋ በታምራት በሐማን ነፍስ በትምህርት ሲናገሩ ።
ወሐንካሳን የሐውሩ ። ሐንካሳን ነፍስ በትምህርት ሲሄዱ ወዕውራን ይሬእዩ ፤ ዕውራን ሥጋ በታምራት ዕውራን ነፍስ በትምርት ሲያዩ አይተው አሕዛብ እስኪያደንቁ ድረስ ፤
ወሰብሕዎ ለአምላከ እስራኤል ዘወሀበ ዘከመዝ ሥልጣነ ለሰብእ ለሰው እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠ ማለት አላመኑም ቢሉ ደግ ነቢይ ያስነሣልን ብለው አምነዋል ቢሉ ሰራሱ ድኅነት ይሻ የነበረ ሥጋን ከባሕርይ ልጅህ ጋራ አዋሕደህ ድኅነትን እንዲያድል ያደረግኸው ብለው የእስራኤልን አምላክ አመስገኑ ።

በእንተ ካልዕ አብዝኆተ ኅብስት ።

፴፪ ወጸውዖሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ያምሀሩኒ እሉ ሕዝብ ማር፡ ፰ ፣ ፩ ።
፴፪ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ እሊህ ሰዎች ያሳዝኑኛል አላቸው ። እስመናሁ ሠሉስ መዋዕል እምዘ በልቡ እከለ እህል ከበሉ ሦስት ቀናቸው ነውና ።
ወአልቦሙ ዘይበልዑ ።
የሚበሉት የላቸውምና ።

ወኢይፈቅድ እፈንዎሙ ርኁባኒሆሙ ።
እንደተራቡ ሳሰናብታቸው አልወድም ።
ከመ ኢይመጽልው በፍኖት ።
ከጉዳና በስልት እንዳይወድቁ

፴፫ ወይቤልዎ አርዳኢሁ እምአይቴ እንከ ለነ በገዳም ኅብስት ዘያጸግብ ለዘመጠነዝ ሕዝብ ።

፴፫ ለዚህን ያህል ሰው የሚበቃ እንጀራ ከወዴት እናገኛለን አሉት ።

፴፬ ወይቤሎሙ ሚመጠን ሐባውዝ ብክሙ ።
፴፬ ምን ያህል እንጀራ አላችሁ አላቸው ።
ወይቤልዎ ሰብዑ ።
ሰባት እንጀራ ። ወኅዳጥ ዓሣ ። አንድ ዓሣ ሎምቢዓሣ አለ አሉት ። ወገባሩ ኅዳጥ እንዲል ።

፴፭ ወአዘዞሙ ለሕዝብ ይርፍቁ ዲበ ምድር ።
፴፭ ሕዝቡን ከምድር ተቀመጡ አላቸው ።
፴፮ ወነሥአ ሰቡዓ ኅብስተ ወዓሣ ።
፴፮ ሰባቱን ኅብስት ዓሣውንም ያዘ ።
ወይእተ ጊዜ እእኵተ ።
ያን ጊዜ አመሰገነ ።
ባረከ ፤ ገመሰ ፤ ወፈተተ ፤ ቈረሰ። ወወሀቦሙ ለአዳርኢሁ ፤ ሰጡ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው ።

፴፯ ወበልዑ ኵሎሙ ወጸግቡ ።
፴፯ ሁሉም በልተው ጠገቡ ። ወዘተርፈ ፍተታተ አግኃሡ ሰብዓተ አስፈሬዳተ ምሉአ ።
መሳይምተ መዛርዓ አክፋረ አስፈሬዳተ ይላል ። የተረፈውን ፯ መሶብ ዕንቅብ ቅርጫት ማለት ነው መልተው አነሱ ።

፴፰ ወእለሰ በልዕዎ የአክሉ ፬ሺህ ዘእንበለ አንስት ወደቅ ።
፴፰ የበሉት ሰዎች ከሴቶችና ከሕፃናት በቀር አራት ሺህ ያህል ይሆናሉ ፤ ሐተታ እንዳለፈው ምዕራፍ ፲፬ ቍ ፳፩ ፤ ሰባት ማንሳታቸው በሰባቱ ዕለታት በ፯ ልዑካን ምሳሌ ፬ሺህ ሰዎች በልተውለት የተረፈው በዘመነ ብሉይ ከተገለጸው ምሥጢር ከራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሰው የተቻለውን ያህል ኍሥቶለት የተረፈው በልበ ነቢያት እንደቀረ ያጠይቃል አምስተኛ አልጨመረላቸውም በግዕዝ እንስሳ ናችሁ ሲል እንጀራውም ገብስ ነው ገብስ ምግበ እንስሳ ነው በግዕዝ እንስሳ አላችሁ ሲል ። አንድም ገዳም በሄዳችሁ ጊዜ ምግብ አታሻሽሉ ለማለት ፤ ካምስቱ አሥራ ሁለት ከሰባቱ ሰባት አነሡ አለ ጥቂቱን ብዙ ብዙውን ጥቂት የማደርግ እኔ ነኝ ሲል ።

፴፱ ወፈቲሖ እሕዛበ ዓርገ ውስተ ሐመር ወሖረ ውስተ ደወለ መጌዶል ።
፴፱ ሕዝቡን አሰናብቶ በመርከብ ተጭኖ ወደ መጌዶል ሄደ ።

ዘከመ ኀሠሡ ትእምርተ እምሰማይ ።

ምዕራፍ ፲፮ ።

፩ ወመጽኡ ኀቤሁ ፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን እንዘ ያሜክርዎ ወይሴአልዎ ትእምርተ እምሰማይ ያርእዮሙ ማር ፰ ፡ ፲፩ ።

፩ ከዚህ በኋላ ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን ሲፈትኑት ከሰማይ ምልክት አሳየን ሲሉት መጡ ሐተታ እንዳለፈው ፡ ምዕ ፲፪ ቍ. ፴፰ ።

፪ ወአውሥአ ወይቤሎሙ እምከመ መስየ ወኮነ ሐዋየ ትብሉ ጽሕወ ብሔር ። ሉቃ ፲፪፡ ፶፬ ።

፪ የመሸ ድግዝግዝታም የሆነ እንደሆነ ብራ ያድራል ትላላችሁ ።
እስመ ያጥየሐይሕ ሰማይ ። ሰማይ አልፎ አልፎ በቀይ ሰብኳልና ።

፫ ወእምከ ጽሕወ ትብሉ ዮምሰኬ ይዘንም ።
የነጋ እንደሆነ ግን ዛሬ ይዘንማል ትላላችሁ ።
እስመ ያጥየሐይሕ ሰማይ ድሙነ ።
ደመና ዳር እስከ ዳር ገጥሞ ይፈልቃልና ።
አ መደልዋን ።
እናንተ ግብዞች ።

፫ ገጸ ሰማይኑ ተአምሩ ፈክሮ ማቴ ፲፪ ፡ ፴፱ ።
ዮሐ ፪ ፡ ፩ ።

፫ የሰማዩን ፊት ማለት የሰማይን ግብር እናውቃለን ትላላችሁ ወተአምረ መዋዕልሰ እፎ ኢተአምሩ በዘመናችሁ የተደረገውን ታምራት አለማወቃችሁ ስለምን ነው ። እንድም እምከመ መስየ ብለሀ መልስ ሥጋ የለበስ ተስፋ የደረሰ እንደሆነ ። ጽሕወ ብሔር ሥጋ አለበሰም ተስፋ አልደረስም ትላላችሁ እስመ ያጥየሐይሕ ሰማይ ፤ የተነገረው ትንቢት የተቆጠረው ሱባዔ ገና ነውና ብላችሁ ። ወእምከመ ጽሕወ ሐሳዊ መሲሕ ግን የተወለደ እንደሆነ ገና ዛሬ ሥጋ ለበሰ ተስፋ ደረሰ ትላላችሁ ። በሐሰት ተጨፍኖ አምላክ ነኝ ብሏልና ። አመደልዋን ፡ እናንተ ግብዞች ገጸ ሰማይኑ ፤ ሰማያዊ ልደቴን እናውቃለን ትላላችሁ ወተአምረ መዋዕልሰ ። በዘመናችሁ የተደረገውን ምድራዊ ልደቴን አለማወቃችሁ ስለምን ነው ።
ወይቤሎሙ ትውልድ ዕሉት ወዘማ ትእምርተ ተኃሥሥ ። ዕምቢተኛ ሴሰኛ ቤተ አይሁድ ምልክትን ትሻለች ። ወትእምርትስ ኢተውህባ ዘእንበለ ትእምርተ ዮናስ ነቢይ ምልክት ግን ዮናስ ካደረገው ምልክት በቀር አይሰጣትም ። ም ፲፪ ቍ ፴፱ ተ መልክት።
ወእምዝ ኃደጎሙ ወሖረ ።
ከዚህ በኋላ ትቷቸው ሄደ ።

በእንተ ብኁአ ፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን ።

፭ ወበጺሖሙ አርዳኢሁ ማዕዶተ ረስዑ ነሢአ ኅብስት ።

፭ ደቀ መዛሙርቱ ወንዙን ተሻግረው ከሄዱ በኋላ እንጀራ ረሱ ግልጥ አለመያዛቸውን ዐወቁ ።

፮ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ዑቁ ወተዓቀቡ እምብሑአሙ ለፈሪሳውያን ።

፮ ጌታ ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ አላቸው [illegible] እንጋ ኅብ [illegible]

፯ እርስ በርሳቸው አሰበው እንጀራ አልያዝን ምን ተጎተቱ ይለናል አሉ ።

፰ ወአእሚሮ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ምንተ ትሔልዩ በበይናቲክሙ አ ሕጹፃነ ሃይማኖት ።

፰ ጌታም አውቆባቸው አናንት ሃይማኖት የሌላችሁ እናንት በናንት ለምን ታስባላችሁ አላቸው ። እስመሁ ኅብስት አልብክሙ ። እንጀራ አልያዛችሁ ምን ተጎተቱ አልኋችሁን ።

፱ ዓዲሁ ኢትሌብዉኑ ወኢትዜክሩ ሀአመ ኃምስ ኅብስት እለ ለ፶ ምእት ። ማቴ ፲፬፡ ፲፱ ዮሐ ፮፡፱ ።

፱ አምስት እንጀራ አበርክቼ ላምስት ሽህ ሰው ባበላሁ ጊዜ የተደረገውን አታስተውሉም አታስቡ ትምን ወሚመጠነ መዛርዓ አግኃሥክሙ ምን ያህል ቅርጫት አነሣችሁ ።

ወይቤልዎ ፲ወ፪ተ ።

አሥራ ሁለት እነሣን አሉት ። አንድም ዘአግኃሥ ክሙ ያነሣችሁት ምን ያህል ነው አላቸው ዐሥራ ሁለት ነው አሉት ።

፲ ወአመኂ ሰብዐ ኅብስተ እለ ለ፬ ምእት ። ማቴ ፲፭፡ ፴፮ ።

፲ ሰባቱን እንጀራ አበርክቼ ላራት ሽህ ሰው ባበላሁ ጊዜ የተደረገውን አታስታውሉም ። ሚመጠነ አስፈሬዳተ አግኃሥክሙ ። ምን ያህል እንቅብ አነሣችሁ አላቸው ፯ አነሣን አሉት ዘአግኃሥክሙ ያነሣችሁት ምን ያህል ነው ሰባት ነው አሉት ።

፲፩ አፎ ዘኢትሌብዉ ከመ አኮ በእንተ ኅብስት እቤለክሙ ተዓቀቡ እምብሑአሙ ለፈሪሳውያን ወሰዱቃውን ።

፲፩ እንዲህ ከሆነ ተዓቀቡ ያልኋችሁ በቁሙ ከፈሪሳውያን ከሰዱቃውያን እርሾ እንዳይደለ እንደ ምን አታውቁ አላቸው ።

፲፪ ወእምዝ ለበው ከመ አኮ ዘይቤሎሙ ይት ዓቀቡ እምነ ብኅዓተ ኅብስት ።

፲፪ ከዚህ በኋላ ተጠበቁ ያላቸው ስለ እርሾ እንዳይደለ ዐወቁ ።

አላ እምነ ትምህርተ ፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን ። ከፈሪሳውያን ከሰዱቃውያን ትምህርት ነው እንጂ ።

በከመ ተአመነ ጴጥሮስ ።

፲፫ ወበጺሖ እግዚእ ኢየሱስ ብሔረ ቂሳርያ ዘፊልጶስ ። ማር ፰፡ ፳፯ ሉቃ ፱፡ ፲፰ ።

፲፫ ጌታ የፊልጶስ ግዛት ከምትሆን ከቂሳርያ አውራጃ በደረሰ ጊዜ በቄሳር ቂሳርያ ተብላለች በጢባርዮስ ጥብርያዶስ በፊልጶስ ፊልጵስዩስ እንደተባለች ። ይህ ፊልጶስ የእስክንድር አባት የሄሮድስ ወንድም ሐዋርያው ፊልጶስ ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ነው ።

ተስእሎሙ ለአርዳኢሁ እንዘ ይብል መነ ይብለኒ ሰብእ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

ወልደ ዕጓለ እመሕያው እኔን ሰው ማን ይለኛል ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው ።

፲፬ ወይቤሉ ቦ እለ ይብሉከ ዮሐንስሃ መጥምቀ

፲፬ ዮሐንስ መጥምቅ ነው የሚሉህ ዮሐንስ መጥምቅ እንደሆንክ የሚናገሩልህ አሉ ። ንጽሕናውን አይተው ።

ወካልዓን ይብሉከ ኤልያስሃ ። ኤልያስ ነው የሚሉህ አሉ ኤልያስ እንደሆንክ የሚናገሩልህ አሉ ድንግልናውን አይተው ወመንፈቆሙ ይብሉከ ኤርምያስ ። ኤርምያስ ነህ የሚሉህ አሉ ። ኤርምያስ እንደሆንክ የሚናገሩልህ አሉ ። ቅድስናውን አይተው ።

ወእመ አኮ ፩ዱ እምነቢያት ቀደምት ።

ይህም ባይሆን ከቀደሙ ነቢያት ማለት ሙሴን ኢያሱን ነው የሚሉህ አሉ አሉት ታምራቱን አይተው ።

፲፭ ወይቤሎሙ አንትሙኬ መነ ትብሉኒ ።

፲፭ እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ ። ከዊነ ይላል አብነት በምን ሀልዎት አለ ትሉኛላችሁ አላቸው ።

፲፮ ወአውሥአ ስምዖን ጴጥሮስ ወይቤ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ። ዮሐ ፮፡ ፷፱—፸ ።

፲፮ ጴጥሮስ እስከ ክርስቶስ ተብሎ የተነገረልህ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ መለሰ ።

፲፯ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፯ ጌታም መለሰ ።

ወይቤ ብፁዕ አንተ ስምዖን ወልደ ዮና ፤

የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ንዑድ ክቡር ነህ ።

እስመ ኢከሠተ ለከ ዘሥጋ ወደም ፤

የኔን አምላክነት ሥጋዊ ደማዊ አእምሮ አልገለጸልህም ። አላ አቡየ ዘበሰማያት ፤ ሰማያዊ አባቴ ገለጸልህ እንጂ ። አንድም ሥጋዊ ደማዊ መምህር አላስተማረህም ሰማያዊ አባቴ አስተምሮሃል እንጂ ።

፲፰ ወአነኒ እብለከ ከመ አንተ ኰኵሕ ፤ ዮሐ ፩፡ ፵፪ ።

፲፰ እኔ መሠረት ነህ ብየ መሠረት እንደሆንህ እናገርልሃለሁ፤ በጥንተ ስብከት አንተኬ ትሰመይ ኬፋ ብሎት ነበርና ያ እንደተፈፀመለት ለማጠየቅ መሠረትነቱ የሃይማኖት የሹመት ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ ።

ባንተ መሠረትነት ምእመንን እንጸታለሁ አጸናታለሁ።

ወአናቅጸ ሲኦልኒ ኢይኄይልዋ አጋንንት አያናውጹዋትም ማለት ድል አይነሱዋትም ። ሐተታ አናቅጽ አላቸው በበር ይወጡበታል ይገቡበታል እንዲገቡበት ጸድቃን ድል ነሥተው ይገቡባቸዋልና እንዲወጡበት ኃጥአን ድል ተነሥተው ይወጡባቸዋልና፣

፲፱ ወእሁበከ መራኁተ ዘመንግሥተ ሰማያት ኢሳ፡፳፪ ፤ ፳፪ ዮሐ ፳ ፡ ፳፫ ።

፲፱ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ማለት ከመንግሥት ሰማያት የምታወጣበት ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታገባበት ሥልጣን እሰጥሃለሁ ፡ የኪዳን የሹመት ፡ ዘአሰርከ በምድር ይኩን እሱረ በሰማያት ። በምድር ያሰርኸው በሰማይ የታሰረ ይሆን ዘንድ ። ወዘፈታሕከ በምድር ይኩን ፍቱሐ በሰማያት ። በምድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆን ዘንድ እንድም ዘአሰርከ በል ፡ በምድር አንድ ያደረግኸው በሰማይ አንድ ይሆን ዘንድ ። ወአሰረ ፪ተ ህላዌያተ እንዲል ወዘፈታሕከ በምድር የለየኸው በሰማይ የተለየ ይሆን ዘንድ ። እንድም ዘአሰርከ በል ፡ ኢደለዎሙ ለእለ አሰርናሆሙ እንዲል ፡ በምድር የቀጸርኸው በሰማይ የተቀጸረ ይሆን ዘንድ ። ወዘፈታሕከ ያሰናበትኸው በሰማይ የተሰናበተ ይሆን ዘንድ ። ይሁን ብየ እንዲሆን እሁበከ በል ።

፳ ወእምዝ አዘዞሙ ለአርዳኢሁ ከመ ኢይንግሩ ወኢለመኑሂ ከመ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፳ ከዚህ በኋላ ክርስቶስ እንደሆነ እንዳይናገሩ ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው ።

ዘከመ ተነበየ ኢየሱስ ሕማሞ ።

፳፩ ወአሚሃ አኀዘ እግዚእ ኢየሱስ ይንግሮሙ ለአርዳኢሁ ፤ ከመ ህለዎ ይሑር ኢየሩሳሌም ።

፳፩ ከዚያ ቀን ጀምሮ ከዚያ ቀን ወዲህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ እንዳለው ለደቀ መዛሙርቱ ይነግራቸው ጀመር ።
ወብዙኀ የሐምምዎ ረበናት ሽማግሎች ብዙ መከራ እንዲያመጡበት ።
ወሊቃነ ካህናት ።
የካህናትም አለቆች ።
ወጸሐፍት ፤
ጸሐፍትም መከራ እንዲያመጡበት ፤
ወይትቀተል ፡ እንዲሞት ፤
ወበሣልስት ዕለት ይትነሣእ ።
በሦስተኛ ቀን እንዲነሣ ይነግራቸው ጀመር ።

፳፪ ወተሠጥዎ ጴጥሮስ ።

፳፪ ጴጥሮስም መለሰለት ።
ወይቤሎ ሐሰ ለከ እግዚኦ ይኩን ላዕሌከ ዝንቱ ።
አቤቱ ይህ ሞት ባንተ ሊደረግ አይገባም አለው ። ።

፳፫ ወተመይጦ ይቤሎ ለጴጥሮስ ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን ። ማርቆስ ፰ ፡ ፴፫ ።

፳፫ ወደ ጴጥሮስ ተመልሶ ሰይጣን ከኋላየ ወግድ አለው ። ጽኑ ባላጋራዬ ሲል ነው ራስ አይቶ የሚመጣ ጠላት ጽኑ ነውና ፡ ወአቀመ ዓይደርሃ ሰይጣነ ላዕለ ሰሎሞን እንዲል ፡ እንድም የምእመናን የነቢያት ጽኑ ባላጋራቸው ሲል ፡ ጌታችን አይሙት ማለት ነቢያትን ሐሰተኞች ማድረግ ነውና ፡ ምእመናንም አይዳኑ ማለት ነውና እንድም ክብዕዓን ወደ ተግሣፅ ተመልሶ ሑር አለው ። ከዚያ እንደ ጊዜ ግብሩ ብፅዓን ሰጪው ከዚህም እንደ ጊዜ ግብሩ ሰይጣን አለው ። እንድም በጴጥሮስ እንጻር ሰይጣንን ሲገሥጽ እንዲህ አለ በአንጻረ በለስ ረገማ ለኃጢአት እንዲል ፡ እስመ ኮንከኒ ሊተ ዕቅፍተ ፡ መሰናክል ሆነህብኛልና ፡ እስመ ኢትሔሊ ዘእግዚአብሔር ዘእንበለ ዘሰብእ ።
ሙቶ ፈርሶ በስብሶ ይቀራል ፤
ትላለህ እንጂ ይነሣል አትለኝምና ፡ እንድም ከሰው ሹመት ሽልማት ትሻለህ እንጂ እግዚአብሔር የሚያወርስህን ክብር አትሻምና ።

ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ኅዲገ ርእሰ በእንተ ክርስቶስ ።

፳፬ ወእምዝ ይቤሎሙ እግዚእ ለአርዳኢሁ ዘይፈቅድ ይትልወኒ ይጽላዕ ነፍሶ ያጥብዕ ወይንሣእ መስቀሎ ሞቱ ወይትልወኒ ። ማቴ ፲፡ ፴፰ ሉቃ ፱፡፳፫፡ ፲፬፡፳፯ ።

፳፬ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊከተለኝ ማለት ሊመስለኝ የሚወድ ሰውነቱን ለመከራ አሳልፎ ሰጥቶ ጨክኖ ነፍሱን ከሥጋው የሚለይበትን መከራ ተቀብሎ በመከራ ይምሰለኝ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው ።

፳፭ ወዘሰ ይፈቅድ ያድኅና ለነፍሱ ለይግድፋ ሉቃ.፲፯፡ ፴፫ ።

፳፭ ዮሐ.፲፪፡ ፳፭ ። ሰውነቱን ሊያድናት የወደደ ይጣላት ።
ወዘገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ ይረክባ ፡ ስለኔ የጣላት ሰውነቱን ያገኛታል ። ትርጓሜ እንዳሰፈው ም. ፲ ቍ፡ ፴፱ ።

፳፮ ወምንተ ይበቍዖ ለሰብእ ለእመ ኰሎ ዓለመ ረብሐ ወነፍሶ ኀጕለ ።

፳፮ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ማለት ፡ ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ በነፍሱ ከተጎዳ ምን ይረበዋል ወምንተ እምወህበ ሰብእ ቤዛሃ ለነፍሱ ምሬረገሃነምን ጣዕመ መንግሥተ ሰማይን ባያውቅ ነው እንጂ ። ቢያውቅማ ለነፍሱ ቤዛ ምን በሰጠ ነበር ፡ ምንት እምኢወሀበ ምን አልሰጥ ባለ ነበር ።

፳፯ እስመ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ይምጻእ በስብሐተ አቡሁ ምስለ መላእክቲሁ ። ግብ. ሐዋ. ፲፯ ፡ ፴፩ ። ሮሜ ፪ ፡ ፮ ።

፳፯ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ለክርስቶስ መላእክትን አስከትሎ ባባቱ ጌትነት ይመጣ ዘንድ አለውና ።

ወአሜን የዓሥዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ ።
ለሁሉም እንደ ሥራው ይሰጠዋል ።

፳፰ አሜን እብለክሙ ቦ እምእለ ህለዉ ይቀውሙ ዝየ እለ ኢይጥዕምዎ ለሞት እስከ አመ ይሬእይዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዘ ይመጽእ በመንግሥቱ ። ማር ፰ ፡ ፴፱ ። ሉቃ ፱ ፡ ፳፯ ።

፳፰ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ በጌትነቱ መንግሥቱ እስኪያዩት ድረስ ከዚህ ቆመው ካሉት የማይሞቱ እንዳሉ በዕውነት እነግራችኋለሁ ሐተታ ደብረ ታቦር አላለፈም ቢሉ የተመቸ አልፉዋል ቢሉ ዮሐንስን ያያል ።

ዘከመ ተወልጠ ኢየሱስ በደብረ ታቦር ።

ምዕራፍ ፲፯ ።

፩ ወእምድኅረ ስሱ መዋዕል ፣ ነሥኦሙ እግዚእ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ እኁሁ ወአዕረጎሙ ደብረ ነዋኀ እንተ ባሕቲቶሙ። ማር ፱ ፡ ፩ ። ሉቃ ፱ ፡ ፳፰ ።

፩ ስለ ሦስት ነገር ያመጣዋል ። አሜን እብለክሙ ቦ እምእለ ህለዉ ይቀውሙ ዝየ እለ ኢይጥዕምዎ ለሞት እስከ አመ ይሬእይዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዘ ይመጽእ በመንግሥቱ ብሎ ነበርና ከዚያ ለማያያዝ ፣ እሞታለሁ ቢለው ቅዱስ ጴጥሮስ ሐስ ለከ ብሎት ነበርና ሎቱ ስምዕዎ ለማለት በባሪያ ቃል የተነገረውን በጌታ ቃል ለማስመስከር ፣ ከመ ፩ዱ እምነቢያት ብለውታልና፣ እግዚአ ነቢያት እንደሆነ ለማጠየቅ የስድስተኛው ድኅር ሰባት ነው ። በቂሳርያ መኑ ይብልዎ ሰብእ ለወልደ እመሕያው ባላቸው በሰባተኛው ቀን ሦስቱን ባለሟሎቹን ለብቻቸው ወደ ተራራ ይዟቸው ወጣ ። ሐተታ ዝቅ ብሎ ቢሆን በነቁ ነበር ። ከፍ ብሎ ቢሆን በዘነጉ ነበርና እመህይ ቀን ሸቶ ። ባለሟሎቹስ እነማናቸው ቢሉ ጌታ እንደ ሰው ወረተኛ ነውን ዋንተ ባለሟሎቹ ናቸው ። እኒህንስ ባለሟል ያደረገበት ምንድነው ቢሉ አልታወቀም ሙሴን ለምስፍና አሮንን ለክህነት የመረጠበት ግብር እንዳልታወቀ እንድም ታውቋል ከህደት በኒህ ጸንቷልና ፣ ጴጥሮስ እሞታለሁ ቢለው ሐስ ማለቱ ሹመት ሽልማት ሽቶ አይደለምን ፣ እኒያስ አሐድነ በየማንከ ወአሐድነ በፀጋምከ ማለታቸው ሹመት ሽልማት ሽተው አይደለምን ።

እንድም ለፍቅሩ ይሳሳሉና በፍቅሩ ይናደዳሉና ጴጥሮስ እመውት ቢለው ሐስ ማለቱ ቢናደድ አይደለምን እኒያስ ትክሉኑ ሰትየ ጽዋዕ ዘአነ እስቴ ቢላቸው አወ ንክል ማለታቸው ቢናደዱ አይደለም ለፍቅሩ ይሳሳሉና በፍቅሩ ይናደዳሉና ፣ ስምንቱን ከእግረ ደብር ትቶ ሦስቱን ይዟቸው ወጥቷል ። ስለምን ቢሉ በይሁዳ ምክንያት ። ይዞት እንዳይወጣ ያእትትዎ ለኃጥእ ከመ ኢይርአይ ስብሐተ እግዚአብሔር ተብሎ ትንቢት ተነግሮበታል ፣ ለይቶም እንዳይተወው ከምሥጢረ መንግሥቱ ቢለየኝ ከሞቱ ከገባሁበት ባለ ነበርና ፣ ነገር ግን በርእሰ ደብር ለሦስቱ የተገለጠ ምሥጢር በእግረ ደብር ላሉ ለስምንቱም ተገልጧል ። በደብረ ሲና ለሰባ ሊቃናት የተገለጸ ምሥጢር በከተማ ላሉ ለኤልዳድ ለሙዳድ እንደተገለጸ ። ተራራ የወንጌል ምሳሌ ተራራ ሲወጡት ያጥራል ከወጡት በኋላ ግን ጭንጫውን ግጫውን ሲያሳይ ደስ ያሰኛል ። ወንጌልም ሲማሯት ታጽራለች ። ከተማሯት በኋላ ግን ጽድቅና ኃጢአት ለይታ ስታሳውቅ ደስ ታሰኛለችና ። እንድም ተራራ የመንግሥተ ሰማያት ተራራን በብዙ ጻዕር እንዲወጡት መንግሥተ ሰማይንም በብዙ መከራ ያገኟታልና ፣ እስመ በብዙኅ ጻማ ሀለወነ ንባእ ለመንግሥተ እግዚአብሔር እንዲል ፣ ተራራውንም ሐዋርያት በሲኖዶስ ታቦር ብለው እንሥተውታል ። በታቦር ያደረገው በሌላ ያላደረገው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ትንቢት ታቦር ወአርሞንኤም በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌ ባርቅ ሲሳራን ድል ነሥቶበታል ። ጌታም በልበ ሐዋርያት ያደረ ሰይጣንን ድል ይነሣበታልና ፣ በተራራ ያደረገው በመንደር ያላደረገው ስለምን ቢሉ በመንደር መካከል አድርጎት ቢሆን ምሥጢር አፈሳ በሆነ ነበርና ። ስለዚህ በተራራ አደረገው ።

፪ ወተወለጠ አርአያሁ በቅድሜሆሙ ።

፪ መልኩ በፊታቸው ተለወጠ ። ወእምድኅረ ውሳጤ ይመጽእ ካልእ ውሳጤ እንዳለው ያለ አይደለም ሦስቱ ከንድ ከስንዝር እካል ምሉእ ብርሃን ሁኑዋል ጽጌያት ከአዕጹቃቸው እንዲፈነዱ ።
ወአብርሃ ገጹ ከመ ፀሐይ ።
እንደ ፀሐይ ብሩህ ሆነ ።
ወአልባሲሁኒ ኮነ ጸዓዳ ከመ በረድ ።
ልብሱ እንደ በረድ ጸዓዳ ሆነ ። ይህ ሁሉ ጌትነቱን ገለጸ ማለት ነው ።

፫ ወናሁ አስተርአዩ ሙሴ ወኤልያስ እንዘ ይትናገሩ ምስሌሁ ።

፫ ሙሴ ኤልያስ ከሱ ጋራ ሲናገሩ ተሰሙ ። ሙሴ ኤልያስ መሆናቸው በምን ታውቋል ቢሉ ሙሴ በልቁትንቱ ኤልያስም በጸጕርነቱ ። በነፍስስ ልቁትንት የሌም ካባ ዕንጦንስ ዘንድ እንኳ ሲላክ ዘፍነው በነፍሱ ይለዋል በአካለ ነፍስ መጥቶ ተርጉሞላቸዋል፤

ብሎ ብሩህ ሁኖ ተወልዷል ይህ ጺጋው ነው አይነሣውምና ኤልያስን ዘጥብሉል በአጽርቅተ እሳት ይለዋል ይህ ጸጋው ነው አይነሣውምና በዚህ ታውቋል ። አንድም ባነጋገራቸው ታውቋል ። ሙሴ የኔን የሙሴን ጌታ ማን ሙሴ ይልሃል እግዚአ ሙሴ ይበሉሀ እንጂ ፤ ኤልያስም የኔን የኤልያስን ጌታ ማን ኤልያስ ይልሃል እግዚአ ኤልያስ ይበሉሀ እንጂ ሲሉ ተሰምተዋል ። አንድም ሙሴ እኔ ባሕር ብከፍል ጠላት ብገድል ደመና ብጋርድ መና ባወርድ እሥራኤልን ከከፋታቸው መልሶ ማዳን አልተቻለኝም ላንተ ግን መልሶ ማዳን ይቻልሃል ። ኤልያስም እኔ ሰማይ ብለጉም እሳት ባዘንም እሥራኤልን ከከፋታቸው መልሶ ማዳን አልተቻለኝም ላንተ ግን መልሶ ማዳን ይቻልሃል ሲሉ ተሰምተዋል ። አንድም ምውቱ ለሕያው ሕያው ለምውት ሲጸልዩ ተሰምተዋል ። ምውቱ ለሕያው አቤቱ ሁሉን ለንስሐ ሳታበቃ በሞት ባትጠራው የሚሻል ይመስለኛል ሲል ሕያው ለምውት የሰው ፍቅር አገብሮህ ልትሞት ወደዚህ ዓለም መጣህን ሲል ። እንዚህንስ ያመጣበት ምክንያት ምንድነው ቢሉ ሙሴ ፊትህን ሳየው እወዳለሁ ቢለው ገጽየስ ኢያስተርኢ ለከ ወድኅረስ ትሬኢ ። መሥዋዕት ሁኜ በምቀርብበት ጊዜ በደብረ ታቦር እገለጽልሃለሁ ብሎት ነበርና ፤ ኤልያስንም አንተስ ትከውነኒ ስምዓ በደኃሪ መዋዕል ብሎት ነበርና ። ስለምን ሁለቱን ከነቢያት ሦስቱን ከሐዋርያት አመጣ ቢሉ ተራራ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ፤ በቤተ ክርስቲያን ብሉይ ሐዲስ እንዲነገሩ ለማጠየቅ ፡ አንድም የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ፤ ነቢያትም ሐዋርያትም አንድ ሁነው እንዲወርሷት ለማጠየቅ ። ከመዓስባን ሙሴን ከደናግል ኤልያስን አመጣ ። ደናግል እንጅ መዓስባን አይወርሷትም ባሉ ነበርና ደናግልም መዓስባንም አንድ ሁነው እንዲወርሷት ለማጠየቅ ። ከምውታን ሙሴን ከሕያዋን ኤልያስን አመጣ ። ንሕነ ሕያዋን የተባሉና ኢንበጽሖሙ ለምውታን የተባሉ አንድ ሁነው እንዲወርሷት ለማጠየቅ ።

፬ ወአውሥአ ጴጥሮስ ወይቤሎ ለእግዚእ ኢየሱስ እግዚኦ ሠናይ ለነ ሀልዎ ዝየ ።

፬ ቅዱስ ጴጥሮስ ከዚህ መኖር ለኛ በጎችን ነው አለው ። አንተ የወትሮ ሥራህን እየሠራህ ብንራብ እያመላኸን ብንታመም እየፈወስኸን ብንሞት እያነሣኸን ። ሙሴ የወትሮ ሥራውን እየሠራ ደመና እየጋረደ መና እያወረደ ባሕር እየከፈለ ጠላት እየገደለ ። ኤልያስ የወትሮ ሥራውን እየሠራ ሰማይ እየለጐመ እሳት እያዘነመ ዝናም እያቆመ በዚህ መኖር ለኛ በጐእችን ነው ወእመሰ ትፈቅድ ንግበር በዝየ ፫ተ ማኅደረ ። ሐስ ለከ ቢለው ገሥጾት ነበርና ቢሆንስ የኔን ነገር አትወድልኝም እንጅ ብትወድልኝስ ከዚህ ሦስት አዳራሽ እንሥራ ። አሐደ ለከ ። አንዱን ላንተ ። ወአሐደ ለሙሴ ፡ አንዱን ለሙሴ ። ወአሐደ ለኤልያስ ፡ አንዱን ለኤልያስ ። ሐተታ እንዚህን ቀኛዝማችነት ግራዝማችነት ይሾሙ ያለ ይመስላል ። የሱን አልተናገረም ቢትወደድነት የለመነ ይመስላል ።

፭ ወእንዘ ይትናገሩ መጽአ ደመና ብሩህ ወጸለሎሙ ። ማቴ ፫፡፲፯ ፡ ፪ ጴጥ ፩፡፲፯ ።

፭ ይኸን ሲናገሩ ብሩህ ደመና መጥቶ ጋረዳቸው ወሶበ ቦኡ ውስተ ደመና ይላል በሉቃስ ንጉሥ በትርሽማ ድንኳን ሳለ በላይ መላጃ ድንኳን ቢተክሉበት ንጉሥ ከድንኳን ገባ እንዲባል ።
ወናሁ መጽአ ቃል እምውስተ ደመና ዘይብል ። ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘቦቱ ሠመርኩ ። ከደመናው ልመለከበት የወደድሁት ለተዋሕዶ የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው የሚል ቃል ተሰማ ።
ወሎቱ ስምዕዎ እሞታለሁ ቢላችሁ አትሞትም እትበሉት ተቀበሉት ።

፮ ወሰሚዖሙ አርዳኢሁ ወድቁ በገጾሙ ።

፮ ደቀ መዛሙርቱ ይኸን ሰምተው ደነገፁ ።
ወፈርሁ ጥቀ ።
ፈጽመው ፈሩ ። ሐተታ ዮሐንስን ደነገጠ አላለውም እንዚህን ደነገጡ አለ እንደምነው ቢሉ ።
ዮሐንስ ፡ አልተጠራጠረምና ደንገጠ አላለውም እንዚህን ተጠራጥረዋልና ደነገጡ አለ ። አንድም አታስደንግጥ ያለው አያሸደነግጥምና ዮሐንስ አልደነገጠም አለ ። አታስደንግፅ ያላለው ያስደነግጣልና እንዚህን ደነገፁ አለ ።

፯ ወቀርበ እግዚእ ኢየሱስ ወገሠሦሙ ።

፯ ጌታ ቀርቦ ያዛቸው ወይቤሎሙ ተንሥኡ ወኢትፍርሁ ።
አይዟችሁ ተነሡ አላቸው ።

፰ ወአንሥኡ አዕይንቲሆሙ ።

፰ ዓናቸውን አቅንተው አዩ ። ወአልቦ ዘርእዩ ወኢመነሂ ዘእንበለ እግዚእ ኢየሱስ ባሕቲቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አዩ እንጂ ማንንም ማን አላዩም ።

፱ ወእንዘ ይወርዱ እምደብር አዘዞሙ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይብል ኢትንግሩ ወኢለመኑሂ ዘርኢክሙ እስከ አመ ወልደ ዕጓለ እመሕያው እሙታን ይትነሣእ ።

፱ ጌታም ከተራራው ሲወርዱ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያያችሁትን የሰማችሁትን አትናገሩ አላቸው ። ሐተታ ውዳሴ ከንቱ አይሻምና የሚያምኑበት ጊዜ አልደረሰምና እስከ ትንሣኤ ፡ አንድም መከራን ወደ ኋላ አድርጎ ክብርን መናገር አይገባምና ። አንድም

ሰውን ሁሉ እየሰበሰበ መንግሥቴን ላሳያችሁ እያለ ምትሐት ያሳያል ሆን ባሉት ነበርና ።

፲ ወተስእልዎ አርዳኢሁ እንዘ ይብሉ እፎ ይብሉ ጸሐፍት ኤልያስ ሀለወ ይምጻእ ቅድመ ፤

፲ መውደቃቸው ሞት መነሣታቸው ትንሣኤ መስሏቸው ጸሐፍት ኤልያስ እስቀድሞ ይመጣ ዘንድ እንዳለው የሚናገሩት እንደምን ነው አሉት ።

፲፩ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፩ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ እወ ኤልያስ ይቀድሞ መጺአ ።
እዎን ኤልያስ አስቀድሞ ይመጣል ።
ወያስተራትዕ ኵሎ ።
ሁሉን ያከናውናል ።

፲፪ ወባሕቱ እብለክሙ ከመ ኤልያስ ወድአ መጽአ ።

፲፪ ነገር ግን ኤልያስ ፈጽሞ መጥቶ እንዳለ ወኢያእመርዎ ።
እንዳላወቁት ማለት እንዳልተቀበሉት እነግራችኋለሁ ወባሕቱ ገብሩ ላዕሌሁ ኵሎ ዘከመ ፈቀዱ ።
የወደዱትን አደረጉበት እንጂ ማለት ዓሰበ ዘማ አደረጉበት እንጂ ወከማሁ ለወልደ ዕጓለ እመሕያውኒ ሀለዎ ይሕምም እምኔሆሙ ።
ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርቶስም እንደሱ ከሳቸው መከራ ይቀበል ዘንድ አለው ።

፲፫ ወእምዝ አእመሩ አርዳኢሁ ከመ በእንተ ዮሐንስ ይቤሎሙ ።

፲፫ ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ገብሩ ላዕሌሁ የነገራቸው ስለ ዮሐንስ መጥምቅ እንደሆነ ዐወቁ ዮሐንስ መጥምቅ ነው አሉ ።

በእንተ ወርኃዊ ዘይጼዓር ።

፲፬ ወበጺሖ ኀበ አሕዛብ ይቤሎሙ ምንትኑ ትትኀሠሥዎሙ ማር.፱፥፲፯ ሉቃ ፱፥፴፰ ።

፲፭ ክሕዝቡ በደረሰ ጊዜ ለምን ታዳክሚቸዋላችሁ አላቸው ። ሐተታ ስምንቱን መምህራችሁ ወዴት ሄደ እያሉ ሲያደክሟቸው ቆይተዋል ።
ወቀርበ ኀቤሁ ብእሲ ወሰገደ ሎቱ እንዘ ይትመሐለል ወይብል ተሣሃል ሊተ ወልድየ ።
ክነገር ያልገባ ሰው ነው ለብቻው ቆይቶ ሰገደለት እቤቱ ልጄን አድንልኝ አለው ።
እስመ እኩይ ጋኔን እኃዞ ቢስ ጋኔን አድሮበታልና ።
ወበአርእስተ አውራኅ ይሣቅዮ ወርኅ እያየ ይጥለዋልና ምልእተ ወርኅ ሲሆን ደም ይመላል ብርድ ብርድ ይላል ደዌ ይቀሰቀሳልና ጨረቃ እንጂ ባታመልኩ ነው ለማለት ።
ወመብዝኅቶሰ ያወድቆ ውስተ እሳት ወቦ እመ ያወድቆ ውስተ ማይ ።
ይልቁንም ብዙ ጊዜ ከእሳት ከወኃ ይጥለዋል ።

፲፮ ወአምጻእክዎ ኀበ አርዳኢከ ።

፲፮ ያድኑልኛል ብየ ወደ ደቀ መዛሙርትህ አመጣሁት ።
ወስዕኑ ፈውሶቶ ።
ማዳን ተሳናቸው ።

፲፯ ወእምዝ አውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፯ ከዚህ በኋላ ጌታችን መለሰ ፡ ወይቤሎ ትውልድ ኢአማኒት ወእሉት ።
እንቢተኛ አሉተኛ ትውልድ ሐዋርያት ፤
እስከ ማዕዜኑ እሄሉ ምስሌክሙ ።
እስከመቼ ከናንተ ጋራ እኖራለሁ ።
ወእስከ ማዕዜኑ እትኤገሠክሙ እስከ መቼ ዝም እላችኋለሁ አላቸው ። ሐተታ ንጉሥ በሌለበት ጊዜ ከንቲባ መሥራት መቅጸት እንዲገባው ባያውቁ መምህራችን በሌለበት ጊዜ አይቻለንም ብለዋልና እስከ መቼ ከናንተ ጋራ እኖራለሁ ንጉሥ ባለ ጊዜ ከንቲባ መሥራት መቅጸት እንዳይገባው ባያውቁ መምራህችን ሳለ ነው እንጂ ብለዋልና እስከ መቼ ዝም እላችኋለሁ ሳለሁማ እኔ አደርገው የለ ምን ሲል እንዲህ አለ ።
አምጽእ ሊተ ዝየ ።
ወዲህ አምጣልኝ አለ ።

፲፰ ወገሠጾ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፰ ጌታ ገሠጸው ማለት ፃዕ መንፈስ ርኩስ አለው ።
ወወፅአ ጋኔኑ እምላዕሌሁ ፡ ጋኔኑ ከሱ ወጣ ።
ወሐይወ ወልዱ በይእቲ ሰዓት ልጁ በዚያች ሰዓት ዳነ ።

፲፱ ወእምዝ ቀረቡ አርዳኢሁ እንተ ባሕቲቶሙ ይቤልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ በእንተ ምንት ንሕነ ስዐነ አውፅኦቶ ።

፲፱ ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ቀርበው እኛ ማስወጣት ስለምን ተሣነን አሉት ።

፳ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ በእንተ ሕጸተ ሃይማኖትክሙ ሉቃ ፲፯ ፥ ፮ ።

፳ ስለ ሃይማኖታችሁ ማነስ ማለት ሃይማኖት ባይኖራችሁ ነዋ አላቸው ።
አማን እብለክሙ እመ ብክሙ ሃይማኖት መጠነ ኀጠተ ሰናፔ ።
እንኳን አይሻም ፍጽምት ናት ፍጹም ሃይማኖት ቢኖራችሁ ወትብልዎ ለዝ ደብር ፍልስ እምዝየ ኀበ ከሀ ወይፈልስ ይህን ተራራ ክዚህ ተነሥተህ ወዲያ ሂድ ብትሉት እንዲሄድ ።
ወእልቦ ዘይሰእነክሙ ።
ቸግሯችሁ የሚቀር እንደሌለ በውነት እነግራችኋለሁ ። ሐተታ ሊጻፍ ባይቻል ነው እንጂ በሱ ጊዜ ተደርጓል በሱ ጊዜስ አልተደረገም በአብርሃም ሶርያዊ ጊዜ የተደረገውን መናገር ነው ። ስሊቀ ጳጳሱ

አንድ አይሁዳዊ ወዳጅ ነበረው ከንጉሡ ተንባላት ወዳጆች ናቸው ያም ሊጠይቅ ያም ሊጠይቅ እየሄዱ ይገናኛሉ እየተከራከሩ ሊቀ ጳጳስ አይሁዳዊን ምላሽ ያሳጣዋል ከዕለታት አንድ ቀን ለብቻው ገብቶ ነገር ሠራ የኒህ የክርስቲያን ሃይማኖታቸው እንጂ ደካማ ነው አለው ። እንኪያ እየተከራከሩ ምላሽ ያሳጧችኋልሳ አለው ።

ለዚህማ ምልክት እንጅል የምትባል መጽሐፍ አለቻቸው ለእመ ብከሙ ትላለች ። አድርጉ ብትላቸው አይሆንላቸውም አለው እሱን ሲያገኘው ነገሩን ያጣዋል ነገሩ ትዝ ሲለው እሱን ያጣዋል ከዕለታት ባንድ ቀን እሱ ባለበተ ነገሩ ትዝ አለው አባቴ የምጠይቅህ ኑሮኝ አንተን ሳገኝህ ነገሩን እያጣሁት ነገሩ ትዝ ሲለኝ አንተን እያጣሁህ ነበር ። አሁን ግን ነገሩም ትዝ ብሎኛል አንተም መጥተሃል አለው ። ምንድነው አለው እንጅል የምትባል መጣፍ አለቻችሁን አለው ። አዎን አለው እንዲህ ትላለች አለው እምን አለው ታደርጋላችሁን አለው ፣ አዎን አለው ሚመጠን አእላፍ ክርስቲያን የዚህ ሁሉ ክርስቲያንንማ ሃይማኖት ተራራ አያህልምን እንኪያስ አድርገህ አሳየኝ አለው ቀን ስጠኝ አለው ሦስት ቀን ሰጠው ሂዶ ከእመቤታችን ሥዕል አመለከተ ልጄ እንዲህ ያለው ሳንተ አይደረግልህም የሚደረግልት ስምዖን ዘሒሒቲ ዓይኑ አለተርታ ሰው መስሎ ከገቢያ ዕንጨት ሲሸጥ ታገኘዋለህ ሂደህ ንገረው እኔን አለችህ በለው ያለዚያ በጅ አይልህም አለችው ቢሄድ እንደ ነገረችው አገኘው እየፈራ ሂዶ በስተኋላው ልብሱን ያዘው አወቀብኝ ብሎ ተቆጣው ምን አድርግ ትለኛለህ በሀገርህ ድኃ አይኖርምን አለው እመቤታችን ልካኝ ነው ብሎ ነገሩን ገልጦ ነገረው ። እንኪያስ እኔን አትግለጠኝ ክርስቲያንን ባንድ ወገን አሕዛብን ባንድ ወገን ሰብስበህ ካህናቱን ልብሰ ተክህኖ አልብሰህ ቆየኝ አንተ እኔ የምሠራውን ሥራ እያየህ ሥራ ሕዝቡ አንተ የምትሠራውን እያዩ ይሥሩ ፴፩ ኪርያላይሶን አድርሰው ሰግደው ሲነሡ ተራራው ተነሣ በውስጡ ተያዩ ሲሰግዱ ይመለሳል ሲነሡ ይነሣል ሦስት ጊዜ እንዲሁ አድርገው ባራተኛው እየወጣ የሚያውካቸው ውኃ ነበር ሂደህ ተጋረድላቸው ብሎት ቦታውን ለቆ ሂዶ ተጋርዶላቸዋል አንድም ለእመ ብከሙ ብለህ መልስ ፤ ሰመዩ ደብረ በእንተ ትዕቢቱ ምንትኑ ዝ ደብር ቅድመ ዘሩባቤል እንዲህ ፤ ደብር የተባለ ዲያብሎስ ነው ፍጹም ሃይማኖት ቢኖራችሁ ሰይጣንን ውጣ ብትሉት ይወጣል ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፳ ወዝንቱ ዘመድ ኢይመፅእ ዘእንበለ በጾም ወጸሎት ።

፳ ይህ አብሮ አደግ ጋኔን ካልጾሙ ካልጸለዩ አይወጣም ። አንድም ይህ ደካማ ባሕርያችሁ ካልጾመ ካይልጸለየ ጋኔን ኢየወፃም ። አንድም ወዘመደ ፍጥረትኒ መሰዎ ለአስሐትያ እንዲል ፣ ይህ የፍጥረት ወገን የሚሆን ሰይጣን ካልጾሙ ካልጸለዩ አይወጣም ።

፳፩ ወእንዘ ያንሶሱ ውስተ ገሊላ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ያግብእዎ ውስተ እደ ሰብእ። ማቴ ፳፣ ፲፰ ማር ፱፣ ፴፩። ሉቃ ፱፣ ፵፬ ።

፳፩ ጌታ በገሊላ ሲመላለስ የሰውን ልጅ ያሲዙት ዘንድ አላቸው ።

፳፪ ማለት እያዛለሁ ። ወይቀትልዎ ።

፳፪ እሞታለሁ ። ወአመ ሣልስት ዕለት ይትነሣእ፣ በሦስት ቀን እነሣለሁ አላቸው ። ወተከዙ ጥቀ እርጓኢሁ ስሚዖሙ ዘንተ ።

ደቀ መዛሙርቱ ይኸን ሰምተው ፈጽመው አዘኑ ።

በእንተ ውሂበ ጸባሕት ።

፳፫ ወበጺሖሙ ቅፍርናሆም መጽኡ እለ ጸባሕተ ዲናር ይነሥኡ እምኀበ ጴጥሮስ ።

፳፫ ቅፍርናሆም በደረሰ ጊዜ ከጴጥሮስ ግብር የሚቀበሉ ሰዎች መጡ ።

ወይቤልዎ ሊቅክሙሰ ኢይጼብሑኑ ጸባሕተ ።

መምህራችሁ አይገብርም አሉት ።

፳፬ ወይቤ እወ ።

፳፬ የኔ መምህር አዎን ይገብራል አዎን አይገብርም አላቸው ።

ወበዊአ ውስተ ቤት አቅደመ እግዚእ ኢየሱስ ብሂሎቶ ከቤት በገባ ጊዜ ጌታ አስቀድሞ ጠየቀው ።

ምንተ ትብል አ ስምዖን ።

ስምዖን ሆይ ምን ትፈርዳለህ ነገሥተ ምድር እምኀበ መኑ ይነሥኡ ጸባሕተ ወጋዳ ።

ነገሥታት ያመት ግብርና እጅ መንሻ ከማን ይቀበላሉ ።

እምኀበ ውሉዶሙኑ ወሚመ እምኀበ ነኪር ።

ከልጆቻቸው ነው ወይም ከሌላ አለው ።

፳፭ ወይቤ እምኀበ ነኪር ።

፳፭ ከሌላ ነው እንጅ ልጆቻቸውማ ይገብሩን ያስገብሩን አለው ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ውሉዶሙሰ እንጋ አግዓዝያንኑ እሙንቱ ።

እንኪያ ልጆቻቸው ነጻ ናቸዋ አለው እኔም ነፃ ነኝ ሲል ነው እንከስ ግዑዝ ውእቱ ወልድ ብሎታል ሊቁ ።

፳፮ ወባሕቱ ከመ ኢያንጉርጉሩ ሑር ውስተ ባሕር ወደይ መቃጥነ ።

፳፮ ነገር ግን እንዳያዝኑ ከባሕር ሂደህ መረብህን ጣል ።

ወዘቀዳሚ አሥገርከ ዓሣ ንሣእ ወክሥት አፉሁ ።

መጀመሪያ የያዝኸውን ዓሣ ወስደህ አፉን ክፈት ማለት ሆዱን ቅደደው ።

ወትረክብ ውስቴቱ ስጢጥራስ ዘውእቱ ፩ቱ ድር ኅም ።
በውስጡም አራት ድሪም ታገኛለህ ። ኪያሁ ንሣእ ወሀቦሙ ህየንቴየ ወህየንቴከ ፡
እሱን ወስደህ ፪ን ስለኔ ፪ን ስላንተ ስጣቸው አለው፡ ሐተታ ቁመቱ ፭ ፭ አይደለም ቢሉ በዘመን ብዛት ቀርቷል ከገበረስ አጉድሎም አይገብር ብሎ የሚዛን ደገኑት ነው ፡ ባሕር የዚህ ዓለም ስጢጥራስ የወን ጌል ምሳሌ ፪ ድርሀም ፩ ክፍል ሁና መጸፉን ያመይቃል ወንጌልን ፐገዙብ አድርገህ ሀየንቴየ አሕ ዛብን ሀየንቴከ እሥራኤልን አስተምር ሲል ነው ከዚያም እንደ ሰውነቱ ገበረ እንደ አምላክነቱ ባሕ ርን አስገበረ ።

በእንተ ክርስቲያናዊት ትሕትና ።

ምዕራፍ ፲፰ ።

፩ ወበይእቲ ሰዓት ቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ ለእ ግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይብሉ መኑ እንጋ የዓቢ በመን ግሥተ ሰማያት ። ማር ፱፡ ፴፫ ። ሉቃ ፱፡ ፵፮። ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ። ከዚያ ብዕዓን ሰጠው ከዚህ ገበረለት ሾመው እንጂ ሾመው ተባብለዋል ።

፩ በዚያች ሰዓት ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው በመንግሥተ ሰማይ በላይ የሚሆን ማነው አሉት ፡

፪ ወጸውዓ ሕፃነ ወአቀመ ማእከሎሙ ።
ብላቴና ጠርቶ በመካከላቸው አቆመው ።

፫ ወይቤ አማን እብለከሙ እመ ኢተመየጥ ከሙ ከመ ዝንቱ ሕፃን ኢትበውኡ ውስተ መንግ ሥተ ሰማያት ። ፩ ቆሮ ፲፬ ፡ ፳ ።

፫ ተመልሳችሁ ከየውሃት ጠባይዓዊ ደርሳችሁ እንደዚህ ሕፃን ካልሆናችሁ መንግሥተ ሰማይ እንዳትገቡ በእውነት እነግራችኋለሁ ።

፬ ወዘአትሐተ ርእሶ ከመ ዝንቱ ሕፃን ውእቱ የዓቢ በመንግሥተ ሰማያት ።

፬ እንደዚህ ሕፃን ሁኖ ራሱን ያዋረደ የመን ግሥተ ሰማይ ባለቤት ይሆናል ። ይህም ትሕትና የሚያስተምርበት ሕፃን አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ነው ። በአንጾኪያ የጴጥሮስ ሦስተኛ ሁኖ ተሹሟል ።
፭ ወዘሂ ተወክፈ ፩ደ ሕፃነ ዘከመዝ በስምየ ኪያየ ተወክፈ ፤
፭ እንደዚህ ሕፃን የሆነውን በኔ ስም የተቀበለ እኔን ተቀበለ ማለት እኔ አድርባታለሁ ።
በእንተ ዘተናገረ ኢየሱስ በሳዕለ ዕቅፍት ።
፮ ወዘሂ አስሐቶ ለ፩ዱ እምእሉ ንኡሳን እለ የአምኑ ብየ ይኄይሶ ከመ ይእስሩ በክሣዱ ማኅረፀ አድግ ወያስጥምዎ ውስተ ልጐተ ባሕር ።

፮ በኔ ካመኑ ምእመናን አንዱን ያሳተ እህያ በመዘውር የሚፈጭበትን ወፍጮ ካንገቱ አስሮ ከጥልቅ ባሕር ቢያሰጥሙት ይሻለዋል ። አንድም ጽኑ ቀኖና ሰጥተው በአንብዓ ንስሐ ቢያሰጥሙት ይሻለዋል ።

፯ አሌ ሎቱ ለዓለም እመንሱት ዘይመጽእ ።
፯ ከሚመጣው መከራ የተነሣ ለሰው ሁሉ ወዮለት ።
እስመ ግብር ይመጽእ መንሱት መከራ ግድ ይመ ጣልና ።
ወባሕቱ አሌ ሎቱ ለውእቱ ብእሲ ዘያመጽእ ለመ ንሱት ።
ነገር ግን ዋዛ ፈዛዛ ተጫውቶ መከራን ለሚያመጣት ለይሁዳ ወዮለት ።

፰ ወእመኒ እዴከ አው እግርከ ታስሕተከ ምትራ ወግድፋ እምላዕሌከ ። ማቴ ፭፡፴ ፡ ማር ፱፡፵፪

፰ እጅህም ብትሆን ወይም እግርህ ብታስትህ ካንተ ቆርጠህ ጣላት ።
እስመ ይኄይሰከ ትባእ ውስተ ሕይወት ሐንካስከ ወጽውስከ እምእንዘ ብከ ፪ አዕዳው ወ፪ እእጋር ትት ወደይ ውስተ እሳት ዘለዓለም ።
ሁለት እጅ ሁለት እግር ኑሮህ ወደ ዘለዓለም እሳት ስትገባ እንካሳ ልምሾ ሁነህ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃልና ።

፱ ወእመሂ ዓይንከ ታስሕተከ ምልኃ ወእው ጽኦ እምላዕሌከ ።

፱ ዓይንህ ብታስትህ አውጥተህ ጣላት ።
እስመ ይኄይሰከ ነቋረከ ትባእ ውስተ ሕይወት እም ትባእ ምስለ ፪ሆን አዕይንቲከ ውስተ እሳተ ገሃነም ሁለት ዓይን ኑሮህ ወደ ገሃነመ እሳት ከምትገባ አንድ ዓይን ኑሮህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና ፡ አንድም ወእመሂ ዓይንከ ብለህ መልስ ኤጲስ ቆጶስህን ብትነቅፈው ሻረው ፤ እስመ ይኄይ ሰከ የነቀፍኸውን ኤጲስቆጶስ ሹመህ ኑረህ ኋላ ገሃነመ እሳት ከምትገባ የነቀፍኸውን ኤጲስ ቆጶስ ሽረህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማይ ብትገባ ይሻልሃ ልና ።

፲ ዑቁ ኢታስተኃቅርዎሙ ለ፩ እምእሉ ንኡ ሳን ። መዝ ፴፫ ፡ ፯ ።
፲ በኔ ካመኑ ምእመናን አንዱን እንዳትንቁ እንዳታቃልሉ አስተውሉ ።
እብለከሙ ከመ መላእክቲሆሙ በሰማያት ወትረ ይሬእዩ ገጾ ለአቡየ ዘበሰማያት ።
መላእክተ ዑቃቢዎቻቸው ያባቴን ፊት ዘወትር ያያሉ ማለት መላእክተ ዑቃቢዎቻቸው በባለሟል ነት እንዳሉ እነግራችኋለሁ እንዳይቀስፏችሁ ማለት ነው ። አንድም መላእክተ ዑቃቢዎቻቸው በባለሟ

ልነት እንዳሉ እሳቸውም በባለሟልነት እንዳሉ እነግራችኋለሁ እንዳያስፈርዱባችሁ ማለት ነው ።

በእንተ በግዕት ዘተሐጕለት ።

፲፩ እስመ መጽአ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ይኅሥሥ ወያድኅን ዘተኃጕለ ፤ ሉቃ ፲፱፥ ፲ ።

፲፩ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ የጠፋውን ሊሻ የተጐዳውን ሊያድን ሰው ሁኖዋልና ።

፲፪ ምንተ ትብሉ ። ሉቃ ፲፭፥፩ ።

፲፪ አንቀጸ ንስሐ ነው ምን ትፈርዳላችሁ ። እመቦ ብእሲ ዘቦቱ ፻ አባግዕ ፤ መቶ በግ ያለው ሰው ቢኖር ወእመ ተገድፈ ፩ እምኔሆሙ ፤ ከመቶው አንዱ ቢጠፋበት ፤ እኮሁ የኃድግ ፺ወ፱ተ ውስተ ገዳም ።

ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ ። ወየሐውር ይኅሥሥ ዘተገድፈ የጠፋበትን ሊፈልግ ይሄድ የለምን ።

፲፫ ወእምከመ ረከቦ አማን እብለክሙ ከመ ይትፌሣሕ በእንቲኣሁ ፈድፋደ እም ፺ወ፱ እለ ኢተገድፉ ።

፲፫ ያገኘው እንደሆን ካልጠፉት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ ጠፍቶ በተገኘው ደስ ይለዋል ብዬ ያስ እንዲ ለው በእውነት እነግራችኋለሁ ።

፲፬ ከማሁ ኢይፈቅድ አቡየኒ ዘበሰማያት ከመ ይትኃጐል ፩ዱ እምእሉ ንኡሳን ።

፲፬ እንደዚህም ሁሉ ሰማያዊ አባቴ ከተነሣሕያን አንዱ ሊጐዳ አይወድም ። አንድም ምንተ ትብሉ ብለህ መልስ ። መቶ በጎች የተባሉ መቶ ነገደ መላእክት ናቸው ከመቶው አንዱ ዲያብሎስ ቢወጣ በሱ ሥፍራ አዳም ቢገባ አዳም ቢወጣ እኮሁ የኃድግ ፤ ባርሕየ መላእክትን ትቶ ባሕርየ አዳምን ገን ዘብ ማድረጉን መናገር ነው ። ኢነሥአ ለዘኒሥአ እመላእክት ዘእንበለ ዳዕሙ እምዘርዓ አብርሃም እንዲል ፤ ወእምከመ ረከቦ ። አዳምን ንስሐ ገብቶ ቢያገኘው አማን እብለክሙ ንስሐ ከማያሻቸው ከመላእክት ይልቅ ንስሐ በሚያሻው በአዳም መመ ለስ ደስ ይለዋል ብዬ በእውነት እነግራችኋለሁ ። ከማሁ ኢይፈቅድ አቡየኒ ዘበሰማያት ከመ ይትኃጐል ፩ዱ እምእሉ ንኡሳን ።

አሁን እንደ ተናገርነው ሰማያዊ አባቴ ከተነሳሕያን አንዱ ሊጐዳ አይወድም ።

በእንተ ዘከመ ይደልዎሙ ለእኃው ተገሥጾ ።

፲፭ ወእመኒ አበሰ ለከ እኁከ ሑር ወገሥጾ ለባሕቲትከ ። ዘሌዋ ፲፱፥፲፯ ። ሲራ ፲፱፥፲፫ ። ሉቃ ፲፯፥፫ ። ያዕ ፭፥፲፱ ።

፲፭ ወንድምህ ቢበድልህ በብቻህ ሁነህ በብቻው አድርገህ ለባሕቲትከ ለባሕቲቱ ለብቻህ ሁነህ ለብቻው አድርገህ ብቻህን ሁነህ ብቻውን አድርገህ ምከረው ወእመ ሰምዓከ ረባሕኮ ለእኁከ ።

የተቀበለህ እንደሆነ ረባኸው ጠቀምኸው ።

፲፮ ወእመሰ ኢሰምዓከ ንሣእ ምስሌከ በዳግም እሐደ ። ዘዳ ፲፱፥፲፭ ። ዮሐ ፰፥፲፯ ። ፪ቆሮ ፲፫፥፩ ። ዕብ ፲፥፳፰ ።

፲፮ ባይቀበልህ ግን በሁለተኛው አንድ ሰው ጨምረህ ምከረው ። አው ፪ተ ።

አናንተን ባይቀበል ሁለት ሰው ጨምረህ አንተ ሦስ ተኛ ሁነህ ምከረው ።

እስመ በአፈ ፪ቱ ወ፫ቱ ሰማዕት ይቀውም ኵሉ ነገር በሁለት ምስክር ነገር ይጸናልና ። ንሣእ እሐደ ፤ በሦስት ምስክር ነገር ይጸናልና ። ንሣእ ፪ተ ። አን ድም ባምስት ምስክር ነገር ይጸናልና ። ንሣእ ፪ተ አው ፫ተ ።

፲፯ ወእመሰ ኢሰምዖሙ ሎሙኒ ንግራ ለቤተ ክርስቲያን ። ፩ ቆሮ. ፮፥፩ ። ፪ተሰሎ ፫፥፲፬ ።

፲፯ እሳቸውንም ባይቀበል ንገሩ ለጉባኤ ይላል የፍርድ መጣፍ ባንድ ደወል ለሚሰበሰቡ ንገሩ እኒያን ባይቀበል ለቤተ ክርስቲያን ንገሩበት ።

ወእመሰ ለቤተ ክርስቲያን ኢሰምዓ ይኩን ከመ አረማዊ ወመጸብሐዊ ። ቤተ ክርስቲያን ንም ባይሰማት እንደ አረማዊ እንደ መጸብሐዊ ይሁን ማለት ይለይ ። ሐተታ ወንድሙን ቢበድል እግዚአ ብሔርን የካደ ይመስል ይለይ ማለቱ ስለምነው ቢሉ ፤ ወንድሙን ከበደለ ከሥጋው ከደሙ ይከለከ ላል ከሥጋው ከደሙ ከተከለከለ እንደ አረማዊ እንደ መጸብሐዊ መሆኑ ነውና ፤ አንድም የሚያየውን ወንድሙን መበደሉ እግዚአብሔርን መበደሉ ነውና

፲፰ አማን እብለክሙ ዘአሰርክሙ በምድር ይኩን እሱረ በሰማያት ። ዮሐ ፳፥፳፫ ።

፲፰ ከምድራውያን ነገሥታት ከሌዋውያን ካህ ናት ወገን ያይደለን መለየቱ እንደምን ይሆናል ትሉኝ እንደሆን በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የ ታ ሰረ እንዲሆን ።

ወዘፈታሕክሙ በምድር ይከውን ፍቱሐ በሰማያት በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ እንዲሆን በውነት እነግራችኋለሁ ። እንዳለፈው ፤ ም ፲፮ ቍ ፲፱

፲፱ ወዓዲ እብለክሙ ለእመ ኃብሩ ፪ እው ፫ እምኔክሙ በውስተ ምድር በእንተ ኵሉ ግብር ዘሰ አሉ ይትገበር ሎሙ በሀበ አቡየ ዘበሰማያት ።

፲፱ ያውስ ቢሆን ጥቂት ነን ብዙ አይደለን መለየቱ እንደምን ይሆንልናል ትሉኝ እንደሆነ ከና ንተ ወገን ስለሚሹት ነገር በዚህ ዓለም ሁለቱ ወይም ሦስቱ አንድ ቢሆኑ በሰማይ አባቴ ዘንድ የሚሹት ነገር ይደረግላቸውዋል ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፳ እስመ ኀበ ሀለው ፪ቱ ወ፫ቱ ጉቡአን በስምየ ሀየ እሄሉ አነ ማእከሎሙ ።

፳ ሁለቱ ሦስቱ በስሜ አምነው አንድ ቢሆኑ አንድ በሆኑበት እኖራለሁ ማለት በአድሬባቸው እኖራለሁና ። ሐተታ ሠልስቱ የተባሉ እንባቢ ተር

ኅሜ መጽሐፍ ናቸው ። አንድም ናዛዚ ተናዛዚ ጌር ላእከ ናቸው ።አንድም ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ናቸው ። ሃይማኖት ትውክልት ተፋቅሮ ናቸው

፳፩ ወእምዝ ቀርበ ጴጥሮስ ወይቤሎ እግዚኦ ሚመጠነ እመ አበሰ ሊተ እኁየ እኅድግ ሎቱ ሉቃ ፲፯፬ ።

፳፩ ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ አቤቱ ወንድሜ ምን ያህል ቢበድለኝ ይቅር ልበለው ። እስከ ስብዕኑ እስከ ሰባት ድረስ ነውን አለው ።

፳፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ኢይብለከ እስከ ስብዕ ።

፳፪ እስከ ሰባት እልልህም ፤ አላ እስከ ሰብዓ በበስብዕ ሰባቱን አንድ ሸባቱን አንድ እያልክ እስከ ሰባ ነው እንጂ ፥ አንድም እስከ ስብዕ በበሰብዓ ሰባውን አንድ እያልክ እስከ ሰባት ነው እንጂ አለው

በእንተ ምሳሌ አግብርት ወፈድዮተ ዕዳ ።

፳፫ ወበእንተዝ እብለክሙ ትመስል መንግሥ ሥተ ሰማያት ብእሴ ንጉሠ ዘፈቀደ ይትሀሰቦሙ ለአግብርቲሁ ።

፳፫ ንስሐ የሚገባ ስለሆነ መንግሥተ ሰማያት ሕገ ወንጌል ፥ ሕገ ወንጌል ተስፋ ፥ ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ብላቴኖቹን ሊቈጣጠራቸው የወደደ ንጉሥን ትመስላለች ።

፳፬ ወሶበ አኀዘ ተሐስቦቶሙ አምጽኡ ሎቱ አሐደ ዘይፈድዮ እልፈ መካልየ ።

፳፬ በተቆጣጣራቸው ጊዜ የእልፍ ወቄት ባለዳ አመጡለት ።

፳፭ ወኃጢኦ ዘይፈድዮ አዘዘ እግዚኡ ይሚጥዎ ምስለ ብእሲቱ ወምስለ ውሉዱ ።

፳፭ የሚከፍለው ቢያጣ ከልጆቹና ከሚስቱ ጋራ ሽጡት ብሎ አዘዘ በወንጌልስ መሸጥም የለ ተገዝቶ ደሞዝ አውጥቶ ይከፈለኝ ሲል ነው ። **ወኵሎ** ዘቦ እስከ ይፈዲ ።

፳፮ እልፍ ወቄት እስኪከፍል ድረስ ።

፳፮ ወወድቀ እንከ ውእቱ ገብር ወሰገደ ሎቱ ወአስተብቍዖ ። ያ ባሪያ ወድቆ ማለደው ፤ እንዘ ይብል እግዚኦ ተዓገሠኒ አቤቱ ታገሠኝ ። ወኵሎ አፈድየከ ። እልፍ ወቄት እከፍልሃለሁ ብሎ ።

፳፯ ወምሕሮ እግዚኡ ለውእቱ ገብር ወዕዳሁኒ ኀደገ ሎቱ ፤

፳፯ ለዚያ ባሪያ ጌታው አዘነለት ዕዳውን ሁሉ ተወለት ።

፳፰ ወወፂኦ ውእቱ ገብር ረከበ አሐደ ገብረ እምነ አብያጺሁ ዘይፈድዮ እልፈ ዲናረ ።

፳፰ ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ወገን የመቶ ወቄት ባለዳ አገኘ ።
ወአኀዞ ወኀነቆ እንዘ ይብል ሀበኒ ዘትፈድየኒ ። ገንዘቤን ስጠኝ ብሎ አስጨንቆ ያዘው ።

፳፱ ወወድቀ ውእቱ ገብር ታኅተ እገሪሁ ወአስተብቍዖ እንዘ ይብል ተዓገሠኒ ።

፳፱ ያ የጌታ ባርያ ታገሠኝ ማለት ቀን ስጠኝ ብሎ ወድቆ ማለደው ፥ ወኵሎ አፈድየከ ።
ጥቂት ጥቂት እያልሁ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ።

፴ ወዓበዮ ወሖረ ወሞቅሖ ፥

፴ ብትከፍለኝ ከፈለኝ ያለዚያ አይሆንም ብሎ አስሮ አጋዘው እስከ ይፈድዮ ፥
እስኪከፍለው ድረስ ።

፴፩ ወርእዮሙ አግብርተ እግዚኡ ዘገብረ ተከዙ ጥቀ ፥

፴፩ የጌታው ባሮች ባልንጀሮቹ ያደረገውን አይተው ፈጽመው አዘኑ ፥
ወሐዊሮሙ ነገርዎ ለእግዚኦሙ ኵሎ ዘገብረ ፥ ሂደው ያደረገውን ሁሉ ለጌታቸው ነገሩት ፥

፴፪ ወእምዝ ጸውዖ እግዚኡ ኦ ገብር እኩይ ኵሎ ዕዳ ኀደጉ ለከ ።

፴፪ ከዚህ በኋላ ጌታው ጠርቶ አንት ክፉ ባርያ ዕዳህን ሁሉ ተውሁልህ ።
እስመ አስተብቋዕከኒ ።

፴፫ ማልደኸኛልና ስለ ማለድኸኝ አኮሁ መፍትው እንተሂ ትምሀር ውእተ ገብረ ቢጾከ በከመ አነ መሀርከከ ።

፴፫ እኔ እልፍ ወቄት እንደተውሁልህ አንተስ ልትተው አይገባህም ነበርን ።

፴፬ ወተምዓ እግዚኡ ወመጠዎሙ ለእለ ይሣቅይዎ ።

፴፬ ጌታው ተቆጥቶ እሱ ለሰው ካላዘነ ብሎ መከራ ሥቃይ ለሚያጸኑበት ሰጠው ።
እስከ አመ ይሜልጥ ኵሎ ዘይፈድዮ ።
እልፍ ወቄት እስኪከፍለው ድረስ ።

፴፭ ከማሁኬ አቡየኒ ሰማያዊ ይገብር ለክሙ እመ ኢኃደግሙ እበሳሆሙ ለቢጽክሙ እምኵሉ ልብክሙ ።

፴፭ እንደዚህም ሁሉ የወንድሞቻችሁን ኃጢአት በፍጹም ልቡናችሁ ይቅር ካላላችሁ ሰማያዊ አባቴም እንዲህ ያደርግባችኋል ። አንድም ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብለህ መልስ።መንግሥተሰማያት አብ መላእክትን ሊቈጣጠራቸው የወደደ ንጉሥን ትመስላለች አለ እሱ ነው ማለት ነው ። ወሶበ አኀዘ ተሀስቦቶሙ። በተቆጣጣራቸው ጊዜ ፍጹም ኃጢአት የሠራ አዳምን አመጡለት ። ወኃጢኦ ዘይፈድዮ ። ሃይማኖት ምግባር ቢያጣበት ። አዘዘ ይሢጥዎ በሱ በሔዋን በልጆቹ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስን ፈረደባቸው። በአዳም ሁሉን መናገር ነው።አንድም መምሀረ ንስሐ ነው ፥ አዘዘ ይሚጥዎ ፥ በሕዋሳቱ ደዌያትን ፈረደበት ፥ ወኵሎ ዘቦ፥ ቀናኖውን እስ

ኪፈጽም ድረስ ። ወወድቀ ወአስተብቍዖ፣ በድየሃለሁ ይቅር በለኝ።ወኵሎ እፈድየከ ፣ ቀኖናየን እፈጽማለሁ አለው ። ወምሀሮ ፣ አዘነለት ፣ ኃጢአቱን አስተሰረየለት ። ወወፂአ ፣ ኃጢአቱ ከተሰረየለት በኋላ ከሕዝቡ አንድ ተነሃሳሂ አገኘ ። ወአኃዞ ወሐነቆ ፣ መጽሐፍ ያዘዘውን ፈጽም ብሎ አስጨንቆ ያዘው ። ወወድቀ ወአስተብቍዖ ፤ ቀኖናየን ልፈጽም ብሎ ማለደው ። ወአበየ ወሞቆሖ ። ብትፈጽም ፈጽም እስዚያ አይሆንም ብሎ አወገዘው ። እስከ ይፈድዮ ፤ ቀኖናውን እስኪፈጽም ድረስ ፤ ወርእዮሙ አብያጺሁ ፣ መላእክት አይተው ፈጽመው አዘኑ ሰው ለሰው እንዲህ ይጨክናል ብለው ፤ ወሐዊሮሙ ነገርዎ ፣ ሂደው የሠራውን ሥራ ሁሉ ለጌታቸው ነገሩት ሐተታ መንገሩስ የለም የነገሩት ዐውቆ ሥራ እንዲሠራ ዐውቆ ሥራ መሥራቱን መናገር ነው ። ወአምዝ ጸውዖ ፣ ከዚህ በኋላ በደዌ ጸራው ። ወይቤሎ ፤ አንተ ክፉ ቄስ እኔ ኃጢአትህን ሁሉ አስተሰረይኩልህ ፤ እስመ አስተብቋዕከኒ ፣ ማልደኸኛልና ስለማለድኸኝ ። አኮሁ መፍትው እኔ ይቅር እንዳልኩህ አንተስ የወንድምህን ኃጢአት ልታስተሰርይለት አይገባህምን ? ተመየጥ አንተ ወአነ ተወከፍኩ ሀየንቴከ ሞተ በከመ ተወከፈ ክርስቶስ ሞተ ህየንቴየ ወህየንተ ኵሎሙ ልትለው አይገባህም ነበር አለው ። ወተምዓ ወመጠዎ ፣ ፈርዶ መከራ ለሚያጸኑበት ለደዌያት ሰጠው ። እስከ ይፈዲ ፣ ቀኖናውን እስኪፈጽም ድረስ ። ወከማሁኬ ፣ የወንድማችሁን ኃጢአት በፍጹም ልቡናችሁ ይቅር ከላላችሁ ሰማያዊ አባታችሁ አሁን እንደተናገርሁት ያደርግባችኋል ።

በእንተ ዘተግኅሠ ኢየሱስ እም ኢየሩሳሌም ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወሶበ ፈጸመ እግዚእ ኢየሱስ ተንሥአ እምገሊላ ወሖረ ወበጽሐ ውስተ ብሔረ ይሁዳ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ። ማር ፲ ፣ ፩ ።

፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ነገር አስተምሮ ከፈጸመ በኋላ ከገሊላ ወጥቶ የዮርዳኖስ ማዶ ወደሚሆን ወደ ምድረ ይሁዳ ደረሰ ።

፪ ወተለውዎ አሕዛብ ብዙኃን ።
፪ ብዙ ሰዎች ተከተሉት ።
ወፈወሶሙ በሀየ ፣ በዚያም አዳናቸው ።
በእንተ ኪዳን ዘኢይትፈታሕ

፫ ወመጽኡ ኀቤሁ ፈሪሳውያን ያመክርዎ ወይበልዎ ። ማር ፲ ፣ ፪ ።

፫ ፈሪሳውያን ሊፈትኑት እንዲህ ሊሉት መጡ ይከውኖሁ ለብእሲ ኅዲገ ብእሲት በኵሉ ዘአበሰት ሎቱ ሳትበስንበት ደረቀች ሰነፈች ብሎ ለሰው ሚስቱን መፍታት ይገባዋልን አሉት ።

፬ ወአውሥአ መለሰ ፣ ወይቤሎሙ ኢያንበብክሙኑ በውስተ ኦሪት ዘከመ ፈጠሮሙ እምትካት ተባዕተ ወአንስተ ። ዘፍ ፩ ፣ ፳፯ ።

፬ ጥንቱን አዳምን ወንድ ሔዋንን ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸው በኦሪት እንደተጻፈ አልተመለከታችሁም አላቸው ። ብእሴ ወብእሲተ ገብሮሙ ተባዕተ ያለውን ብእሴ አንስተ ያለውን ብእሲተ አለ ።

፭ ወይቤ ወበእንተዝ የኃድግ ብእሲ አባሁ ወእሞ ወይትልዋ ለብእሲቱ ዘፍ፪፣ ፳፬ ። ፩ ቆሮ ፮፣ ፲፮ ። ኤፌ ፭ ፣ ፴፩ ።

፭ ስለዚህ ነገር ሰው አባት እናቱን ትቶ ሚስቱን ተከትሎ ይሄዳል ። ሐተታ ፣ ቆላ ብትሆን ቆላ ይወርዳል ደጋ ብትሆን ደጋ ይወጣል ። አንድም እሱ ፈቃድ ቢነሣበት በናቴ ላድርገው አይልም እሷም ፈቃድ ቢነሣባት ባባቴ ላድርገው አትልምና አንድም በግብር አንድ ይሆናሉና ። ወይትለዋ አፃግዓ ቀርሜሎስ እንዲል ይትሳጸዋ ሲል ፤ ወይከውኑ ፪ ሆሙ አሐደ ሥጋ አንድ አካል ይሆናሉ በግብር አንድም ወንዶች ቢወልዱ ያንተ ናቸው ሴቶች ቢወልዱ ያንቺ ናቸው አይባባሉምና ። አንድም እሱን ቢመስሉ ያንተ ይሁኑ አትለውም እሷን ቢመስሉ ያንቺ ይሁኑ አይላትምና ፣ አንድም በዚህ ዓለም ሳሉ በሕጋቸው ጸንተው ዐሥራት በኩራት ቀዳምያት አውጥተው እንግዳ ተቀብለው ሥጋውን ደሙን በሚገባ ተቀብለው ቢኖሩ በወዲያውም አንድ ዓለም ወርሰው አንድ ፀሐይ ሞቀው ይኖራሉና ።

፮ ናሁኬ ኢኮኑ ፪ተ ።
፮ እነሆ ሁለት አይባሉም ።
አላ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ ።
አንድ አካል ናቸው እንጂ ።
ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ ሰብእ ኢይፈልጥ ።
እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይም አትለይ ሲል ነው ።

፯ ለምንት እንከ አዘዘ ሙሴ የሀብዋ መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ወይድኃርዋ ፣ ዘዳ ፳፬ ፣ ፩ ።

፯ እንዲህ ከሆነ ሙሴ የምትፈታበትን ነውር የሚናገር ደብዳቤ ሰጥቶ ይፍታት ብሎ ለምን አዘዘን አሉት ።

፰ ወይቤሎሙ ሙሴሰ አዘዘክሙ በከመ እከየ ልብክሙ ትድኃሩ አንስቲያክሙ ።

፰ ሙሴስ እንደ ልቡናችሁ ክፋት ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ አዘዛችሁ ።
ወእምፍጥረትስ አኮ ከማሁ ዘተገብረ ።
ጥንቱን ግን የታዘዘው እንዲህ አይደለም አላቸው ሐተታ ። አንዲት ሴት ላንድ ወንድ አንድ ወንድ ላንዲት ሴት ነው እንጂ የሞተችበት የሞተባት በፈቲው ዖር የሚናደዱ ሆኑ ። ሙሴ ወደ እግ

ዚአብሔር ቢያመለከት የሞተበት ያግባ ብሎታል ሲጸላት ጊዜ ወንዱ ልቧን እያሸ የሚገድላት ሆነ ሴቲቱም መርዝ አጠጥታ ሥራይ አብልታ የምትገድለው ሁናለችና እንዲህ አለ ።

ወእንሂ እብለክሙ ሆሉ ዘይድኅር ብእሲቶ ዘእንበለ ትዘመ ለሊሁ ረሰያ ዘማ ማቴ፭ ፥ ፴፪ ። ማር ፲ ፥ ፲፩። ሉቃ ፥ ፲፮ ፥ ፲፰ ፥ ፩ቆሮ ፥ ፯ ፥ ፲ ።

፱ እኔም ሳትሰስንበት ደረቀች ሰነፈች ብሎ ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ ዘማ አሰኛት ብየ እነግራችኋለው ።
ወእንተ ደኃርኖ ዘእውሰበ ዘመወ ።
በነውር የተፈታችኖቱንም ያገባ በደለ ።

፲ ወይቤልዎ አርዳኢሁ እመ ከመዝ ውእቱ ሥርዓተ ብእሲ ወብእሲት ኢርቱዕ አውስቦ ።

፲ የባልና የሚስት ሥራት እንዲህ ከሆነ ማለት ሰነፈች ደረቀች ብሎ መፍታት የማይገባ ከሆነ ሊያገቡ አይገባም አሉት ።

፲፩ ወይቤሎሙ አኮ ለኵሉ ዘይትከሃል ዝንቱ።
፲፩ ይህ ንጽሕ ጠብቆ መኖር ለሁሉ አይቻልም ዘእንበለ ለዘተውህቦ ።

ሀብተ ንጽሕ ለተሰጠው ግዕዛኑ ለጸናለት አራቱ ባሕርያት ለተስማሙለት ነው እንጂ
፲፪ እስመቦ ሕፅዋን እለ ከማሁ ተወልዱ እምከርሠ እሞሙ ።
፲፪ ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ ሕፅዋን ሁነው የተወለዱ አሉና እንደ እባ ባይሉል ልጆች ሙጻዓ ስንት ብቻ ነበራቸው ።
ወቦ ሕፅዋን እለ ሐፀውዎሙ ሰብእ ።
ኃላ ሻንቅላ ሕፅዋን ያደረጋቸው አሉና ለኒያ ነው እንጂ ወቦ ሕፅዋን እለ ሐፀው ርእሶሙ በእንተ መንግሥተ ሰማያት ።
ከቤተ መንግሥት እንበላለን እንጠጣለን ብለው ሕፅዋን የሆኑ አሉ ለኒያ ነው እንጂ ።
ሐተታ ፥ ይህስ አይደነቅም እህያን አልተዋጋም በሬን አልተራገጠም ብሎ ። እስመ ቦ ሕፅሕን ከናታቸው ማኅፀን ሕፅዋን ሁነው የተወለዱ አሉና ለኒያ ነው እንጂ ፤ እለ ኤርምያስ ቀደስኩከ እምከርሠ እምከ እንዲል ፤ ወቦ እለ ሐፀውዎሙ ሰብእ ። መምህራን መክረው አስተምረው ንጹሐን ያደረጓቸው አሉና ለኒያ ነው እንጂ ። ሙሴ ኢያሱን ኤልያስ ኤልሳዕን ወቦ እለ ሐፀው ርእሶሙ በእንተ መንግሥተ ሰማያት ፤ ባሕርያቸው ደካማ ነውና አይችሉትም ብሎ ነው እንጂ ከሕገ ሥጋ ሕገ ነፍስ ከሕገ እንስሳ ሕገ መላእክት እንዲበልጥ ታውቆ የለም መንግሥተ ሰማያትን እንወርሳለን ብለው ንጽሕ ጠብቀው ከሴት ርቀው የሚኖሩ አሉና ለኒያ ነው እንጂ ወዘሰ ይከል ተዓግሦ ለይትዓገሥ ።

መታገሥ የሚቻለው ማለት ንጽሕ ጠብቄ ከሴት ርቄ እኖራለሁ የሚል ግን ንጽሕ ጠብቆ ከሴት ርቆ ይኑር ።
በእንተ ሕፃናት እለ መጽኡ ኀበ ኢየሱስ ፤
፲፫ ወእምዝ አምጽኡ ሎቱ ሕፃናተ ከመ ያንብር እዴሁ ላዕሌሆሙ ወይጸሊ ። ማር ፲ ፥ ፲፫ ሉቃ ፲፰ ፥ ፲፭ ።
፲፫ ከዚያ በኋላ እጁን ይጭንባቸው ዘንድ ማለት በአንብሮተ እድ ይባርካቸው ዘንድ ሕፃናትን ይዘው መጡ ። በኤልሳዕ ልማድ ሕፃናት መጥተው ዕርግ በራህ ብለው ዘበቱበት ሁለት ድባት አስነስቶ ፵፪ ሕፃናት አስፈጀ የነቢየ እግዚአብሔር መርገሙ እንዲህ የጕዳ በረከቱ እንደምን ይጠቅም ብለው እያመጡ የሚያስባርኩ ሁነዋልና በዚያ ልማድ አመጡለት ።
ወገሠጽዎሙ አርዳኢሁ ለእለ አምጽእዎሙ ።
አባቶቻቸው ያመጧቸው ሕፃናትን ተቆጧቸው ይጠቀጥቁናል ብለው ፤ አንድም ሕፃናትን ያመጧቸው አባቶቻቸውን ተቆጧቸው ትምህርት ያስፈቱናል ብለው ።

፲፬ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኅድግዎሙ ለእሉ ሕፃናት ኢትከልእዎሙ ይምጽኡ ኀቤየ ማቴ ፲፰ ፥ ፫ ።

፲፬ ወደኔ ይመጡ ዘንድ ሕፃናትን ተዋቸው አትከልክሏቸው እለ እስመ ለዘከመ እሉ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት ።
መንግሥተ ሰማያት ወንጌል የምትነገር እንደነዚህ ላሉ ነውና አንድም መንግሥተ ሰማያት የምትወረስ እንደነዚህ ላሉ ነውና ።

፲፭ ወአንበረ እዴሁ ላዕሌሆሙ ወኃለፈ እምህየ ።

፲፭ እጁን ጭኖ ባርኳቸው ከዚያ ሄደ እነዚህም ከ፹፫ የሚበዙ ናቸው ከነህም ከፍጹምነት ያልደረሰ ሊቀ ጳጳስነት ጳጳስነት ኤጲስቆጶስነት ያልተሾመ የለም ከነዚህም አንዱ እግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ነው ።

በእንተ ወሬዛ ባዕል ።

፲፮ ወናሁ መጽአ ፩ ብእሲ ወይቤሎ ሊቅ ኄር ምንተ እግበር እምሥናያት ከመ አረስ ሕይወተ ዘለዓለም ። ማር ፲ ፥ ፲፯ ሉቃ ፲፰ ፥ ፲፰ ።
፲፮ አንድ ሰው መጥቶ መምህር የማታልፍ መንግሥተ ሰማያትን እወርስ ዘንድ ከበጎ ነገር ወገን ምን ላድርግ አለው ።
፲፯ ወይቤሎ ምንተ ትብለኒ ኄር ።
፲፯ እላመንም ብሎ ሳታምንብኝ ለምን ኄር ትለኛለህ አለው ። አንድም ኄር ብለው ኄር ይለኛል ብሎ በተንኮል መጥቷልና የሕሊናውን

አውቆቧት ኄር ብለው ኄር ይለኛል ብለህ ለምን ኄር ትለኛለህ ።
አልቦ ኄር ዘእንበለ ፩ እግዚአብሔር ።
ካንድ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም አለው ።
ወእመሰ ትፈቅድ ትባእ ውስተ ሕይወት ዕቀብ ትእዛዛተ ። ወደ ሕይወት ማለት መንግሥተ ሰማያት ትገባ ዘንድ ከወደድህስ ሕግጋትን ጠብቅ ዘፀ ፳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ።

፲፰ ወይቤሎ አይቴኑ ዕቀብ ።
፲፰ ማን ማን ልጠብቅ ። ዘአዓቅቦን የምጠብቃቸው ማን ማን ናቸው አለው ።
ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ኢትቅትል ነፍሰ ።
ጌታም ነፍስ አትግደል ።
ኢትዘሙ ። አትሰስን ።
ኢትስርቅ ። አትስረቅ ።
በሐሰት አትመስክር ።

፲፱ አክብር አባከ ወእመከ ።
፲፱ አክብር ማለት አባትህን እናትህን ርዳ ።
ወአፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ ።
ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ አለው ።

፳ ወይቤሎ ወሬዛ ዘንተሰ ኵሎ ዓቀብኩ እምንዕስየ ።

፳ ይህንስ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄያለሁ፤ ምንት እንከ ተርፈኒ ።
ምን ቀረኝ ዘተርፈኒ የቀረኝ ምንድነው አለው ።
ወነጸሮ እግዚእ ኢየሱስ ወአፍቀሮ ።
ጌታ አይቶ ወደደው ።

፳፩ ወይቤሎ አሐቲ ተርፈተከ ።
፳፩ አንዲት ቀርታሃለች አለው ።
እመሰ ፈቀድከ ፍጹመ ከመ ትኩን ሑር ወሢጥ ኵሎ ጥሪተከ ወሀብ ለነዳያን ።
ፍጹምነትስ ከወደድህ ሂደህ ገንዘብህን ሁሉ ሽጠህ ለነዳያን ስጥ አለው ።
ወታጠሪ መዝገበ ዘበሰማት በሰማይ መዝገብ ታገኛለህ ማለት መንግሥተ ሰማያትን ትወርሳለህ ። ሐተታ አርድና ከምጽዋት ነገረው ሑር ሢጥ ብሎ አርድና ሀብ ብሎ ምጽዋትን ። አንድም ነዳያን ላም በሬ ፈረስ በቅሎ ቢሰጧቸው ወጥቶ ወርዶ መሸጥ አይሆንላቸውምና ፤ ዳግመኛ የከብቱን ዋጋ የሚያውቅ ባለቤቱ ነውና ፤ እንዳነኙ እንዳይጥሉት ።
ወነዓ ትልወኒ ።
ለጊዜው በእግር ተከተለኝ ፍጻሜው በግብር ምሰለኝ አለው ።

፳፪ ወሰሚዖ ወሬዛ ዘንተ ነገረ ወሐረ እንዘ ይቴክዝ ።
፳፪ እሱም ይኸን ነገር ሰምቶ እያዘነ ሄደ ።
እስመ ብዙኅ ጥሪቱ ። ገንዘቡ ብዙ ነውና ። ሢጥ ቢለው ሰንቱን ይሸጣል ብሎ አንድም እሱን መከተል ሽቶ ነበርና ሑር ቢለው ። አንድም ፍጹምነት ሽቶ ነበርና አሐቲ ተርፈተከ ቢለው ።

፳፫ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ አማን እብለክሙ ከመ ባዕል እምዕጹብ ይበውእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ።

፳፫ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ባለጸጋ ጨርሶ መጽውቶ በጭንቅ መንግሥተ ሰማያት ይገባል ብየ እንዲገባ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ።

፳፬ ወካዕበ ዕብለክሙ ይቀልል ይኅልፍ ገመል እንተ ሰቍረተ መርፍዕ እምባዕል ይባእ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፳፬ ዳግመኛ ባለጸጋ መንግሥተ ሰማይ ከሚገባ ገመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል ብየ እነግራችኋለሁ ፤ ሐተታ ባይጸፍ ነው እንጂ በሱ ጊዜ ተደርጓል ። በሱ ጊዜስ አልተደረገም ደቀ መዝሙሩ ታዴዎስ ያደረገውን መናገር ነው ይህን ቢያስተምር ነጋድያን ገመል ጭነው መጡ በቃል ያስተማርኸንን አድርገህ አሳየን አሉት አንጥረኛ ወዳጅ ነበረውና መርፌ ስደድልኝ አለው ነገሩን አስቀድሞ ሰምቷልና ቀዳዳውን አስፍቶ ሰደደለት ምን ቢሰፋ ገመል ያሳልፋል ያንተንም ዋጋ እግዚአብሔር አያስቀርብህ እንደጥንቱ አድርገህ ስደድልኝ አለው እንደጥንቱ አድርጎ ሰደደለት ሦስት ጊዜ እያመላለሰ አሳይቷቸዋል አንድም አይሁዳዊ አምኖ ተጠምቆ መንግሥተ ሰማያት ቢገባ አረማዊ አምኖ ተጠምቆ መንግሥተ ሰማያት ከገባ ይቀላል ብየ በውነት እነግራችኋለሁ አይሁዳዊ አያደርገውም አረማዊ ያደርገዋል ማለት ነው ።
፳፭ ወሰሚዖሙ አርዳኢሁ አንከሩ ጥቀ እንዘ ይብሉ መኑ እንጋ ይክል ድኂነ ።
፳፭ ደቀ መዛሙርቱ ይኸን ሰምተው ገንዘቡን ሁሉ ጨርሶ መጽውቶ መንግሥተ ሰማያት መግባት ለማን ይቻለዋል ብለው ፈጽመው አደነቁ ። አንድም ታምራት ማድረግ ለማን ይቻለዋል ብለው አደነቁ ።
፳፮ ወነጸሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ በኀበ ሰብእ ኢይትከሀል ዝ ።
፳፮ ጌታ አይቷቸው ታምራት ማድረግ በሰው ዘንድ አይቻልም
ወበኀበ እግዚአብሔርሰ ኵሉ ይትከሃል ።
በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ይህ ሁሉ ይቻላል ። አንድም እግዚአብሔር ባላደረበት ሰው ዘንድ አይቻልም ። እግዚአብሔር ባደረበት ሰው ዘንድ ግን ይቻላል ። አንድም ገንዘቡን ጨርሶ መመጽወት እግዚአብሔር ላላደረበት ሰው አይቻልም እግዚአብሔር ላደረበት ሰው ግን ይቻላል ።

በእንተ ዘኪመ ይደልዎሙ ዕሤት ለእለ ይተልውዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፳፯ ወእምዝ አውሥአ ጴጥሮስ ወይቤሎ ናሁ ንሕነ ኀደግነ ኵሎ ወተሎናከ ምንተ እንከ ንረክብ ።

፳፯ ጴጥሮስ መለሰ እኛ ሁሉን ትተን ተከትለንሃል ምን እናገኝ ይሆን አለው ፤ ሐተታ ምን ነበረውና እንዲህ አለ ቢሉ አንድ አህያ አንድ በሬ መረቡን መርከቡን ትቶ ተከትሎታልና ይህ ሁሉ አይደለም እከብራለሁ ባይ ልቡናውን ትቶ ተከትሎታልና እንዲህ አለ ።

፳፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አንትሙ እለ ተለውክሙኒ አመ ዳግም ልደት አመ ይነብር ወልደ ዕጓለ እመሕያው ዲበ መንበረ ስብሐቲሁ ።

፳፰ ሰው በሆንኩ ጊዜ ያመናችሁብኝ እናንተ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ በዕርገት በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ በኖረ ጊዜ ።
ወአንትሙኒ ትነብሩ ዲበ ፲ቱወ፪ቱ መናብርት ።
ባሥራሁለቱ ነገደ እሥራኤል በመምህርነት ትሾማላችሁ ፤
ወትኴንኑ ፲ተ ወ ፪ተ ሕዝበ እሥራኤል ።
ዐሥራ ሁለቱን ነገደ እሥራኤልን ታስተምራላችሁ እንድም አመ ይነብር ውስተ ዓለም ሐዲስ ይላል ያመናችሁብኝ እናንተ በዕለተ ምጽአት ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ በጌትነት በተገኘ ጊዜ ባሥራ ሁለቱ ወንበር ትቀመጣላችሁ ዐሥራሁለቱ ነገደ እሥራኤል ትፈርዳላችሁ ። ያን ጊዜስ መቀመጥም መፍረድም የለም ዛሬ የፈረዱት ፍርድ የማይቀርባቸው ስለሆነ እንዲህ አለ ፤

፳፱ ወኵሉ ዘኃደገ አብያቴ ወአኃወ ወአኃተ አበ ወእመ ወብእሲተ ወውሉደ ወገራውኀ በእንተ ስምየ ምእተ ምክዕቢተ ይነሥእ ፤
፳፱ በኔ ስም አምኖ በኔ ስም ስላመነ አባቱን እናቱን እኅቱን ሚስቱን ቤቱን ንብረቱን ርስቱን የተወ ሁሉ መቶ ዕጥፍ ያገኛል አለ ሐተታ መቶ እናት አባት መቶ እኅት ወንድም መቶ ሚስት ያገኛል ማለት አይደለም በዚህ ዓለም ያባትነትየናትነትየወንድምነት የእኅትነት የሚስትነት ሥራ ይሠራለታል ሲል ነው ። ወሕይወተ ዘለዓለም ይወርስ ። በወዲያው የዘለዓለም ሕይወት መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል ፤
፴ ወብዙኃን ቀደምት ይከውኑ ደኃርተ ወደኃርት ይከውኑ ቀደምተ ። ማቴ ፳ ፡ ፲፮ ማር ፡ ፲ ፡ ፴፩ ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፴ ።
፴ ኋለኞች ፊተኞችን ፊተኞች ኋለኞችን ይሆናሉ ማለት ቀደምት ጸሐፍት ፈሪሳውያን ደኃርት ሐዋርያትን ይሆናሉ አለ ዓሥራቱን በኵራቱን እጥተው ደኃርት ሐዋርያት ቀደሞት ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ይሆናሉ አለ አግኝተው ፤ እንድም ቀደምት ሐዋርያት ደኃርት ሠለስቱ ምእትን ደኃርት ሠለስቱ ምእት ቀደምት ሐዋርያትን ይሆናሉ ኋላ በሥራ ያስፉታል እንጂ በጥምቀት በሚገኘው ክብር አንድ ናቸውና ።

በእንተ ምሳሌ ዘዓቀብተ ወይን ።

ምዕራፍ ፳ ።

፩ እስመ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብእሴ በዓለ ቤት ዘወፅአ ነግሃ ይትዓሰብ ገባእተ ለዐጸደ ወይኑ ።

፩ መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ሕገ ወንጌል ተስፋ ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ለወይኑ ቦታ ምንደኞችን ሊስማማ ማለዳ የወጣ ባለ ቤትን ትመስላለችና ቀደምት ወይከውኑ ደኃርተ ደኃርት ይከውኑ ቀደምተ ላለው ። እንድም ትመስላለች እኮን ።

፪ ወተካሃሎሙ በበዲናር ለለዕለት ።
፪ በቀን ድሪም ድሪም እሰጣችኋለሁ ብሎ የተስማማቸውን ወፈነዎሙ ውስተ ዐጸደ ወይኑ ይትቀነዩ ።
ወይን ጨብቆ ብሎ ወደ ወይኑ ቦታ የላካቸውን ባለቤት ትመስላለች ፤ ሐተታ ነግህ የተባለ ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ሰባት ዓመት ያለው ዘመን ነው እስከዚያ ሥራት አይሠራባቸውም መምህረ ንስሐ የሚይዙ ጾም የሚጀምሩ ከዚያ በኋላ ነውና ።

፫ ወወፂኦ ጊዜ ፫ቱ ሰዓት ርእየ ካልዓነ እንዘ ይቀውሙ ውስተ ምሥያጥ ጽሩዓነ ።
፫ በሦስት ሰዓት ቢወጣ ሌሎችን ሥራ ፈተው ካደባባይ ቆመው አገኘ ።
፬ ወሎሙኒ ይቤሎሙ ሑሩ አንትሙኒ ውስተ ዓጸደ ወይንየ ወተቀነዩ ወዘረትዓኒ እሁበክሙ ።
፬ እናንተውንም ከወይኔ ቦታ ሂዱችሁ ወይኔን ጠብቁ የቀናኝን እሰጣችኋለሁ አላቸው ።
በኋላ የመጣን የቀናኝን እሰጥሃለሁ ማለት ልማድ ነው ።
ወእሙንቱ ሖሩ ።
እሳቸውም ሔዱ ።
፭ ወወፂኦ ጊዜ ስሱ ወተሱዓት ሰዓት ገብረ ከማሁ ።
፭ ዳግመኛም በቀትር በተሣት ወጥቶ ሥራ ፈትተው ካደባባይ ቆመው አገኘ ፤ እናንተም ሂዱችሁ ወይኔን ጠብቁ የቀናኝን እሰጣችኋለሁ አላቸው ።
፮ ወጊዜ አሠሩ ወ፩ ሰዓት ወጺአ ረከበ ካልዓነ እንዘ ይቀውሙ ።
፮ በሠርክ ወጥቶ ሌሎችን ሥራ ፈተው ካደባባይ ቆመው አገኘ ።
ወይቤሎሙ ለምንት ቆምክሙ ዝየ ኵሎ ዕለተ ጽሩዓኒክሙ ።

ቀኑን ሁሉ ሥራ ፈታችሁ ለምን ቆማችኋል አላቸው ፤ ከዚያው ገብቶ ከተቆጠረ ብሎ ኵሎ ዕለተ አለ ። አንድም ኵሎ ሰዓተ ሲል ነው ። ዐሥራ ሁለቱን ሰዓተ መዓልት ሥራ ፈታችሁ ለምን ቆማችኋል አላቸው ።

፯ ወይቤልዎ እስመ አልቦ ዘተዓሰበነ ።
፯ የተስማማን የለምና የተስማማን ባይኖር ነው አሉ ።
ወይቤሎሙ ሑሩ አንትሙኒ ውስተ አጸደ ወይንየ ተቀነዩ ወዘረትዓኒ እሁበክሙ ።
እናንተም ሄዳችሁ ወይኔን ጠብቁ የቀናኝን እሰጣችኋለሁ አላቸው ። ሠለስት የተባለ ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ያለው ዘመን ነው ። ቀትር ከሃያ እስከ አርባ ያለው ነው ።
ተሳት ካርባ እስከ ስሳ ያለው ዘመን ነው ። ሠርክ ከስሳ እስከ ሰማንያ ያለው ዘመን ነው እስከዚያ ድረስ ሃይማኖት ሳይማሩ ምግባር ሳይሠሩ ኑረው ከዚህ በኋላ በመምህራን አድሮ አስተምሮ በቃለ መጻሕፍት ገሥጾ ምግባር እንዲሠሩ ሃይማኖት እንዲይዙ ማድረግ ነው ።

፰ ወሶበ መሰየ ይቤሎ በዓለ ዓጸደ ወይን ለመጋቢሁ ጸውዖሙ ለገባእት ወሀቦሙ ዓስቦሙ

፰ ሲመሽ የወይን ባለቤት ሹሙን ጠርቶ ለምንደኞች ዋጋቸውን ሰጣቸው አለው ።
ወእኀዝ ቅድመ እምቀደምት እስከ ደኃርት ።
ከገባእተ ሠርክ ጀምረህ እስከ ገባእተ ነግህ ስጥ አለው

፱ ወመጽኡ እለ ዐሠርቱ ወ፩ ሰዓት ።
፱ ገባዕተ ሠርክ መጡ ።
ወነሥኡ በበዲናር ።
ድሪም ድሪም ሰጣቸው ።

፲ ወመጽኡ ቀደምት ።
፲ ገባዕተ ነግህ መጡ ።
ወመሰሎሙ ዘያበዝኅ ሎሙ ውሂበ ።
አብዝቶ የሚሰጣቸው መሰላቸው ነበር ።
ወወሀቦሙ ሎሙኒ በበዲናር ።
ለሳቸውም ዲሪም ዲሪም ሰጣቸው ።

፲፩ ወነሢኦሙ አንጐርጐሩ ላዕሌሁ ለበዓለ ቤት ።
፲፩ ተቀብለው በባለቤቱ አዘኑበት ።
፲፪ እንዘ ይብሉ እሉ ደኃርት አሐተ ሰዓተ ተቀንዩ ወአስተዓረይኮሙ ምስሌነ ለእለ ጾርነ ክበዶ ወላህባ ለዕለት ።

፲፪ የዕለት ጻሯን ጋሯን ትኩሳቷን ማለት ጧት ጀምረን እስከ ማታ ስንደክም ከዋልነ ከኛ ጋራ ገባእተ ሠርክን አስተካከልሃቸው ብለው አዘኑ ።
፲፫ ወይቤሎ ለ፩ እምኔሆሙ ዓርክየ ኢዓመፅኩከ

፲፫ ከገባእተ ነግህ አንዱን ወዳጄ አልበደልሁህም አለው ።
አኮኑ በበዲናር ተከሃልኩከ በድሪም ተስማምቼህ አልነበረም ።

፲፬ ወንሣእ ዘይረከበከ ወሑር ።
፲፬ የሚገባህን ይዘህ ሂድ አለው ።
ወፈቀድኩ ለዝ ደኃራዊ እሁቦ ከማከ ።
በኋላ ለመጣው ለዚህ እንዳንተ ልሰጠው ወድጃለሁና ።

፲፭ ወሚመ ኢይደልወኒኑ ዘፈቀድኩ እግበር በንዋይየ ።

፲፭ ወይም በገንዘቤ የወደድሁትን ማድረግ አይገባኝምን ።
አው ዓይንከኑ ሐማሚ ውእቱ ዓይንህ ምቀኛ ናት ማለት አንተስ ምቀኛ ነህን ።
ወአነስ ኄር ።
እኔ ግን ቸር ነኝ ማለት ምቀኛ አይደለሁም ።

፲፮ ከማሁኬ ይከውኑ ደኃርት ቀደምተ ወቀደምት ደኃርተ ።

፲፮ እንደዚሁም ሁሉ ገባእተ ሠርክ ገባእተ ነግህን ገባዕተ ነግህ ገባዕት ሠርክን ይሆናሉ ።
እስመ ብዙኃን ጽውዓን ወኅዳጣን ኅሩያን ።
ጥቂትም ሁነው ብዙም ሁነው የተጠሩ የተመረጡ ናቸውና ካጠገቡ ሳለው ቀደምት ይከውኑ ደኃርተ ወደኃርት ይከውኑ ቀደምተ ሳለው አርእስት ሰጥ አንድም ወሶበ መሰየ ብለህ መልስ ፤ ምጽአት በደረሰ ጊዜ እምጸኢ ዓለማት ፈጣሬ ዓለማት አብ መጋቢሁ ወልድን እምጸኢ ዓለማት ፈጣሬ ዓለማት ወልድ መጋቢሁ መልአኩን ምእመናንን ጠርተህ ከኋለኞች ጀምረህ እስከ ፊተኞች ስጥ አለው ። ወመጽኡ እለ ዐሠርቱ ወ፩ዱ ሰዓት ፤ ኋለኞች መጡ ወነሥኡ በበዲናር ። እንደ ሥራቸው ሰጣቸው ወመጽኡ ቀደምት ፊተኞች መጡ ወመሰሎሙ በቀዲመ አቅማናት በአብዝኆ ገድላት የሚያበልጥላቸው መሰላቸው ነበር ። ወወሀቦሙ ሎሙኒ ለሳቸውም እንደ ሥራቸው ሰጣቸው ። ወነሢኦሙ አን ጐር ጐሩ ማዘን የለም ነገሩ የሚያሰኝ ስለሆነ ነው እንጂ ዋጋቸውን ተቀብለው ፍርዱን አደነቁ ። እሉ ደኃርት አሐተ ሰዓተ ተቀንዩ ጥቂት ሰዓት መከራ የተቀበሉ እሊህን ብዙ ዘመን መከራ ከተቀበልን ከኛ ጋራ አስተካከላቸው ብለው አደነቁ ። ፤ ወይቤሎ ለ፩ እምኔሆሙ ዓርክየ ፤ ከደኃርት ጻድቃን አንዱን ወዳጄ አልበደልሁህም አለው ።
መፍቀሬ ሰብእ ነውና ዓርክየ ይለዋል ወፈቀድኩ ለዝ ደኃራዊ እሁቦ ከማከ ወሚመ ኢይደልወኒኑ እግበር ዘፈቀድኩ በንዋይየ ። እንዲህ ማለት ይህን ተናግሮ ዕንጦንስን ከአስካፍ መቃሪን ከክል

ሎቱ አንስት አየጸን ከፍላዊ ትሩፍ ቤበኑዳን ከፈያ ታይ መዓንዝር መስደዱን መናገር ነው ።

እው ዓይንከኑ ሐማሚ እስመ አነ ኄር እንዲህ ማለት ገባእተ ሠርክን ከገባእተ ነግህ ገባእተ ነግህ ገባእተ ነግህን ከገባእተ ሠርክ ማለቱ ኋለኞችን ከፊተኞች ፊተኞችን ከኋለኞች ያቡተካከለበትን ፍርዱን ክፉ ብቁር የሚያውቀው አለ መናሩን መናገር ነው ። ከማሁኬ አሁን እንደ ተናገርኩት ገባእተ ሠርክ ገባእተ ነግህን ገባእተ ነግህ ገባእተ ሠርክን ይሆናሉ ። እስመ ብዙኃን ፣ ብዙም ሁነው ጥቂትም ሁነው የተጠሩ የተመረጡ ናቸውና ቀደምት ይከውኑ ደኃርተ ደኃርት ይከውኑ ቀደምት ላለው ለላይኛው ስጥ ። ም ፣ ፲፱ ፣ ቁ ፣ ፴ ።

ሐተታ ፣ ነግህ የተባለ ዘመነ አበው ነው ሠለስት ዘመነ መሳፍንት ቀትር ዘመነ ነገሥት ተሰዓት ዘመነ ካህናት ሠርክ ዘመነ ሥጋዌ ነው ። አንድም ነግህ የተባለ ዘመነ አዳም ። ሠለስት የተባለ ዘመነ አብርሃም ቀትር ዘመነ ሙሴ ተሰዓት ዘመነ ዳዊት፣ ሠርክ ፣ ዘመነ ክርስቶስ ቀደምት ይከውኑ ደኃርተ ደኃርት ይከውኑ ቀደምት አለ ። በአቤል ጊዜ የነበሩ በዕለተ ዓርብ ያሉትን በዕለተ ዓርብ ያሉት በአቤል ጊዜ የነበሩትን ይሆናሉ ። አንድም በዓጸደ ነፍስ ያሉት በዓጸደ ሥጋ ያሉትን በዓጸደ ሥጋ ያሉት በዓጸደ ነፍስ ያሉትን ይሆናሉ ። አንድም ነግህ ዘመነ ክርስቶስ ፣ ሠለስት ዘመነ ሐዋርያት ቀትር ዘመነ ሰማዕታት ተሰዓት ዘመነ ሊቃውንት ሠርክ ዘመነ መነኩሳት ዘመነ ሐዋርያትና ዘመነ ክርስቶስ አንድ ወገን ነው ብሎ ፣ ሠለስት ዘመነ ሰማዕታት ቀትር ዘመነ ሊቃውንት ሰዓት ዘመነመነኩሳት ሠርክ ዘመነ ደኃርት ጻድቃን በዕለተ ዓርብ ያሉት በዕለተ ምጽአት ያሉትን በዕለተ ምጽአት ያሉት በዕለተ ዓርብ ያሉትን ይሆናሉ ። አንድም ንሕነ ሕያዋን የተባሉት ኢንበጽሖሙ ለምውታን የተባሉት ንሕነ ሕያዋን የተባሉትን ይሆናሉ ።

በእንተ ትንቢት ሣልሲት ዘሕማማት ።

፲፯ ወእንዘ የዓርግ ኢየሩሳሌም ነሥኦሙ ለ፲ ወ፪ቱ አርዳኢሁ እንተ ባሕቲቶሙ ። ማር ፣ ፲ ፣ ፴፪ ሉቃ ፣ ፲፰ ፣ ፴፩ ።

፲፯ ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን አስከትሏቸው ሄደ ።
ወአግኃሦሙ እምፍናት ።
ከመንገድ ፈቀቅ አደረጋቸው ፣ሐቀታ ፣ ወቀደሞሙ በፍኖት ይላል በማርቆስ ፣ በፊት ያሉት በኋላ ነው በኋላ ያሉት በፊት ነው ሲሉ ቀድሟቸው ተገኝቷል እንዲህ ሲሆን እሞታለሁ ይላል ብለውታል ።
፲፰ ወይቤሎሙ ናሁ ንዓርግ ኢየሩሳሌም ።
፲፰ ኢየሩሳሌም እወጣለሁ ።
ወይእኅዝዎ ለወልደ ዕጓለ እመ ሕያው ።
ወልደ ዕጓለ እመሕያውን ይይዙታል ማለት እያዛለሁ ።
ወያገብእዎ ኀበ ሊቃናት ወጸሐፍት ።
ለሊቃናት ለጸሐፍት አሳልፈው ይሰጡኛል ።
ወይኬንንዎ በሞት ።
ይሙት በቃ ይፈርዱብኛል ።

፲፱ ወይሜጥውዎ ለሕዝብ ።
፲፱ ለሕዝብ አሳልፈው ይሰጡኛል ወይሳለቁ ላዕሌሁ ።
ይዘብቱብኛል ።
ወይቀስፍዎ ።
እገረፋለሁ ።
ወይሰቅልዎ ።　እሰቀላለሁ ።
ወይቀትልዎ ።
እሞታለሁ ።
ወይትነሣእ በሣልስት ዕለት ።
በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ አላቸው ።

በእንተ ደቂቀ ዘብዴዎስ ።

፳ ወእምዝ መጽአት ኀቤሁ እሞሙ ለደቂቀ ዘብዴዎስ ምስለ ደቂቃ ማር ፣ ፲ ፣ ፴፭ ።

፳ ከዚህ በኋላ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ማርያም ባውፍልያ ልጆችዋን አስከትላ መጣች ።
ወሰገደት ሎቱ እንዘ ትስእል እየማለደች ሰገደችለት ። ሐተታ ፣ እንዲያው አይደለም ኢየሩሳሌም ሊወጣ ሆነ የሹመት ነገር አንድ ጊዜ ከተደላደለ በኋላ ያስቸግራልና ሂደሽ ተናገሪልን ለዘመድሽ ብለዋታል ፣ ወይቤላ ምንተ ትፈቅዲ እግበር ለኪ ምን ላደርግልሽ ትወጃለሽ አላት ።

፳፩ ወትቤሎ ረሲ ሊተ ከመ ይንበሩ እሉ ደቂቅየ ፩ዱ በየማንከ ወ፩ዱ በፀጋምከ በመንግሥትከ

፳፩ በመንግሥ ጊዜ እኒህ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱ በግራህ እንዲቀመጡ አድርግልኝ ማለት አንዱን ቀኛዝማች አንዱን ግራዝማች በልልኝ አለችው ።

፳፪ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤላ ኢተአምሩ ዘትስእሉ ።

፳፪ የምትለምኑትን አታውቁም ማለት የባለጸጋ ልጅ ኃዘን ቢነግሩት እደን እንዲሉ እሞታለሁ እሰቀላለሁ ብላችሁ ሹመት ሽልማት ትለምናላችሁ አለ ትክሉኑ ሰትየ ጽዋዕ ዘአነ እሰቲ ወጥምቀተኒ ዘአነ እጠመቅ ትጠመቁኑ ።
በዚያውስ ላይ የኔን ጽዋ ትጠጣላችሁ የኔን ጥምቀት ትጠመቃላችሁ ማለት እኔ የምሞተውን ሞት ትሞታላችሁ አላቸው ። ሐተታ ጽዋዕ ጥምቀት አለው ሞቱን ። ጽዋ በተራ እንደሆነ ሞትም በተራ ነውና ጽዋ እንዲያፋቅር ሞቱም ያፋቅራልና ጽዋ

ፈጥኖ እንዲጨለጥ ፈጥኖ ተነሥቷልና ወእሕጸረ ፣ ዕድሜ ልርእሱ እንዲል ።

ጥምቀት እንዲያነጻ ሞቱም መንጽሒ ነውና
ወይቤልዎ እወ ንክል ፣
አዎን ይቻለናል አሉት ሐተታ ፣ ለጌታ የሚያደር ሰው ሞትህን ሞት ሕይወትህን ሕይወት አደርጋ ለሁ ማለት ልማድ ነውና ። እንድም ለፍቅሩ ይሳሳሉ በፍቅሩ ይናደዳሉና ።

፳፫ ወይቤሎሙ ጽዋዕየሰ ትሰትዩ ወጥምቀትየኒ ትጠመቁ ።

፳፫ ጽዋየን ትጠጣላችሁ ጥምቀቴን ትጠመቃላችሁ ማለት ሞቴንስ ትሞታላችሁ ። ወነቢረሰ በየማንየ ወበፀጋምየ አኮ አነ ዘእሁብ ። በግራና በቀኝ መቀመጥ ግን የምሰጥ እኔ አይደለሁም ማለት ቀኛዝማችንነት ግራዝማችንነት የምሾም እኔ አይደለሁም ዘእንበለ ዘአስተዳለወ ሎሙ አቡየ ዘበሰማያት ሰማያዊ አባቴ ላዘጋጀላቸው ለነገሥታት ነው እንጂ አእምሮ ከመ ልዑል ይኬንን መንግሥተ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ወዘፈቀደ ይሁብ እስመ ኢይሠየም መኰንን ዘእንበለ እምኀበ እግዚአብሔር ይል የለም ቢሉ አልመጣሁበትም ሲል እንዲህ አለ ። እንድም በቀኝ በግራ ሁነን እንሰቀል ትላላችሁን በቀኝ በግራ መሰቀል ለናንተ አይደለም ሰማያዊ አባቴ በትንቢት ላዘጋጀላቸው ለፈያታዊ ዘየማን ለፈያታይ ዘፀጋም ነው እንጂ ። እንድም ትክልኑ ብለህ መልስ ። በክብር እንኑር ትላላችሁን እንግዲህስ ወዲህ በክብር መኖር ለናንተ ብቻ አይደለም ለምእመናን ሁሉ ነው እንጂ ወለዲያቆናትኒ በፀጋሙ እንዲል ።

፳፬ ወሰሚያሞሙ ፲ቱ አንጐርጐሩ ላዕለ ፪ቱ አኃው ።

፳፬ ዐሥሩ ይኸን ሰምተው በሁለቱ ወንድማማቾች አዘኑ ዛሬስ ከዚህ እኑረውን ሹመት ይካሰሱብን ጀመር ብለው ።

፳፭ ወጸውዖሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ኢተአምሩኑ ከመ መኳንንቶሙ ለአሕዛብ ይኬንንዎሙ ወዓበይቶሙ ይቀንይዎሙ ።

፳፭ ጌታ ጠርቶ አሕዛብን ነገሥታቱ እንዲገዟቸው ሹማምንቱ እንዲያዟቸው አታውቁምን አላቸው ፤
፳፮ ወለከሙሰ አኮ ከማሁ ።
፳፮ ለናንተ ግን እንዲህ አይደለም ።
፳፯ ወባሕቱ ዘይፈቅድ እምኔክሙ ይኩን ዓቢየ ይኩንክሙ ገብረ ወዘኒ ይፈቅድ እምኔክሙ ይኩን ሊቀ ይኩንክሙ ላዕከ ።
፳፯ ከናንተ ወገን ገዥ ሊሆን የወደደ ሰው ተገዥ ይሁናችሁ በላይ ሊሆን የወደደም አገልጋይ ይሁናችሁ እንጂ ።

፳፰ እስመ ኢመጽአ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ከመ ይትለአክዎ ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ ይትለአክ ወየሀብ ነፍሶ ቤዛ ብዙኃን ።

፳፰ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ሊያገለግል እንጂ ሊያገለግሉት ቤዛ ሊሆን እንጂ ቤዛ ሊሆኑት አልመጣምና ፤ እንዲህም ባለ ጊዜ ፍቅረ ሢመትን አጥፍቶላቸዋል ሁለቱ እኛ የምንገዛቸው መስሎን ነው አንጂ የማንገዛቸው ከሆነ ሹመት ለምናችን ብለዋል ፀሥሩም የሚገዙን መስሎን ነው እንጂ የማይገዙንማ ከሆነ ቢሾሙ ምንዳችን ብለዋል ።

፳፱ ወእንዘ ይወፅእ እምኢያሪኮ ተለውዎ ሰብእ ብዙኃን ።
፳፱ ከኢያሪኮ ወጥቶ ሲሄድ ብዙ ሰዎች ተከተሉት ።

በእንተ ዕውራን ዘኢያሪሆ ።

፴ ወናሁ ፪ቱ ዕውራን ይነብሩ ጥቃ ፍኖት ።
፴ ሁለት ዕውራን እነሆ ከመንገድ ባጠገብ ተቀምጠው ነበር ። ወሰሚያሞሙ ከመ እግዚእ ኢየሱስ የኃልፍ ጸርሑ ።
ጌታ ሲያልፍ ሰምተው አሰምተው ተናገሩ ።
ወይቤልዎ ተሣሃለነ እግዚእ ወልደ ዳዊት ።
የዳዊት ልጅ አቤቱ እዘንልን አሉት ።
፴፩ ወሰብእሰ ይጌሥጽዎሙ ከመ ያርምሙ።
፴፩ ሰዎች ግን ዝም በሉ ይሏቸው ነበር ። ታምራት ይደረጋል ሰው ይሳባል ወንጌል ትሰፋለች አሪት ትጠፋለች ብለው ።
ወአዕበዩ ጸሪሐ እንዘ ይብሉ ተሣሃለነ እግዚእ ወልደ ዳዊት ባይን ዋዛ ብለው የዳዊት ልጅ አቤቱ እዘንልን ብለው አሰምተው ተናገሩ ።
፴፪ ወቆመ እግዚእ ኢየሱስ ወጸውዖሙ ።
፴፪ ለዕውር ርቆ መሄድ አይሆንለትምና ቁሞ ጸራቸው ።
ወይቤሎሙ ምንተ ትፈቅዱ እግበር ለክሙ ።
ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ አላቸው ።
፴፫ ወይቤልዎ ከመ ይትከሠታ አዕይንቲነ ።
፴፫ ዕውር ምን ይሻል ቢሉት ብርሃን እንዲሉ አቤቱ ዓይናችን ይበራልን ዘንድ እንወዳለን አሉት።
፴፬ ወአምሐርም ለእግዚእ ኢየሱስ
፴፬ ጌታችንን አሳዘኑት ።
ወገሠሦሙ አዕይንቲሆሙ ።
ዓይናቸውን ዳሰሳቸው ።
ወበጊዜሃ ነጽሩ ።
በዳሰሳቸውም ጊዜ አዩ ።
ወተለውዎ ።
ለጊዜው በእግር ተከተሉት ፍጻሜው በግብር መሰሉት ከ፫ አርድዕት ገብተው ተቈጠሩ ። እንድም ወእንዘ ይወፅእ እምኢያሪኮ ብለህ መልስ ከልዕ

ልና ወደ ትሕትና በመጣ ጊዜ ነቢያት በግብር መሰሉት ወናሁ ፪ቱ ዕውራን ይነብሩ ጥቃ ፍኖት ፤ ባሕታውያን ክዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በበረሃ አሉ ። ፍኖት ሐተታ እንዳለፈው ምዕ ፳ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ባሕታውያንን ዕውራን አላቸው ከማየት ተከልክለዋልና ። ምሥጢር ገና አልተገለጸላቸውምና ፤ ወሰሚዖሙ ጌታ በዚኃ እንዲገለጥ ምሥጢር እንዲገለጥ ብሎተው ።

ወይቤልዎ ተማኅለነ ምሥጢር ግለጥልን አሉት ወሰብአሰ ፤ አጋንንት ግን ገድላቸውን ያስተዋቸው ዘንድ መከራ ያጸኑባቸው ነበር በማደረጃቸው ሰብእ አላቸው ። ወአዕበዩ ጸሪሖ ፡ አጋንንቱን ድል ነሥተው አመለከቱ ። ወቆመ በዚኃ ተገለጠላቸው ።

ወይቤሎሙ ምን ባደርግላችሁ ትወዳላችሁ አላቸው ከመ ይትከሠታ ፤ ምሥጢር ሊገለጥልን እንወዳለን አሉት ። ወተሠሥዐ ምሥጢር ገለጠላቸው ወበጊዜሃ ፤ ያን ጊዜ ዐወቁ ። ወተለውዎ ፤ ባሕታውያን በግብር መሰሉት ።

ዘከመ ቦአ እግዚእ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም

ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወቀሪቦ ኢየሩሳሌም በጽሖ ቤተ ፋጌ እንተ ገቦ ደብረ ዘይት ፤ ማር ፲፩፡፩፡ ሉቃ ፲፱፡ ፩፡ ፱ ።

፩ ወደ ኢየሩሳሌም ሊገባ በቀረበ ጊዜ የደብረ ዘይት አጠገብ ከምትሆን ቤተ ፋጌ ደረሰ ። ገቦ ይላል ትግሬ አጠገብ ሲል ፋጌ ፎናና የተመሳቀለ ጐዳና ማለት ነው ።

ወሶበሃ ፈነወ እግዚእ ኢየሱስ ፪ተ እምአርዳኢሁ ።

ያን ጊዜ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ ።

፪ ወይቤሎሙ ሖሩ ሀገረ ዘቅድሜክሙ ።

፪ በፊታችሁ ወዳለ ሀገር ሂዱ ። ወይእተ ጊዜ ትረክቡ ዕድግተ ዕሥርተ ምስለ ዕዋላ ።

ያን ጊዜ አህያ ከውርንጭላዋ ጋራ ታስራ ታገኛላችሁ ።

ፍትሕዎን ወአምጽእዎን ሊተ ። ፈታችሁ አምጡልኝ አላቸው ሐተታ ፤ ሰው ሁሉ ከማእሰረ ኃጢአት የሚፈታበት ጊዜ እንደደረሰ ለማጠየቅ ።

፫ ወእመቦ ዘይቤለክሙ ምንተ ትገብሩ ።

፫ ምን ታደርጋላችሁ የሚላችሁ ሰው ቢኖር በሉ እግዚኦሙ ይፈቅዶሙ ። ጌታቸው ይሻቸዋል በሉ በተፈጥሮ ጌታቸው ነውና እንዲህ አለ ።

ወበጊዜሃ ይፈንዎሙ ።

ያን ጊዜ ያሰናብቷችኋል ።

፬ ወዝ ኩሉ ዘኮነ ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ

፬ በነቢይ በልዋ ለወለተ ጽዮን ነዋ ንጉሥኪ ጻድቅ ወየዋህ ይመጽእ ኀቤኪ እንዘ ይጼዓን ዲበ ዕድግት ወዲበ ዕዋላ ።

፭ ይህ ሁሉ የተደረገ ጻድቅ

፭ የባሕርይ አምላክ የዋህ ኃዳጊ በቀል ንጉሥሽ በዕዋል በዕድግት ተቀምጦ ይመጣል ብላችሁ ለጽዮን ልጅ ንገሯት ብሎ ነቢዩ የተናገረው ቃል ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው ።

ሐተታ ፤ ወለተ እሥራኤል ናቸው ጽዮን ኢየሩሳሌም ናት ፤ በሀገሪቱ ሰዎቹን መናገር ነው ልጅ ያግሬ ልጅ የጎጃም እንዲሉ አንድም ወለት አይለወጥም ጽዮን ሕግ ናት እናት ልጆቹዋን ሠርታ ቀጥታ እንድታሳድግ ሕግም ሕዝቡን ሠርታ ቀጥታ ታኖራለችና ። ቃለ ነቢያት ያለ እንደሆነ አያሳትትም በልዋ ለወለተ ጽዮን ያለ ኢሳይያስ ይመጽእ ንጉሥኪ ያለ ዘካርያስ ነውና፡ ቃለ ነቢይ ያለ እንደሆኑ የሁለቱ ስም ነውና ፤ ቃ ለኢሳይያስ ይላል አብነት ኢሳይያስ እንደ አባት እንደ መምህር ዘካርያስ እንደ ልጅ እንደ ደቀ መዝሙር ናቸውና ።

፮ ወሖሩ አርዳኢሁ ገብሩ በከመ አዘዞሙ እግዚእ ኢየሱስ ።

፯ ወአምጽኡ ሎቱ ዕድግተ ምስለ ዕዋላ ።

፮ ደቀ መዛሙርቱ ሄደው እንደ አዘዛቸው
፯ አደረጉ አህያ ከውርንጭላዋ ጋራ አመጡለት ።
ወረሃኑ አልባሲሆሙ ላዕሌሆን ።
ልብሳቸውን ጉዝጉዘሉት ። ሐተታ ፤ ኮርቻ ይቀረቁራል ልብስ አይቀረቁርም የማትቀረቁር ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል ፤ አንድም ልብስ በአካል ያለውን ነውር ይሰውራል ። አንተም ከባቴ አበሳ ነህ ሲሉ ፤
ወተጽዕነ እግዚእ ኢየሱስ ዲቤሆን ።
በሁለቱም ጌታ በጥበብ ፩ ጊዜ ተቀመጠባቸው ።

ሐተታ ፤ ከኢየሩሳሌም እስከ ቤተ መቅደስ ፤ ፲፰ ምዕራፍ ነው ። ፲፮ቱን በእግሩ ሄዶ ሁለቱን በዕድግት ሄዷል በዕዋል ሁና ቤተ መቅደስን ፫ ጊዜ ዞሯል ። የምስትንት ምሳሌ ፤ ፀሥራራቱን በእግሩ መሄዱ ፲ ቃላት ፮ቱ ኪዳናት ኪዳነ ኖኅ ከሆነተ መልክ ጼዴቅ ግዝረተ አብርሃም ጥምቀተ ዮሐንስ ነው ። አንድም ፭ቱን ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ባራት ባራት መቶ ዘመን ቢቈጽሩት ዐሥራ አራት ሊሆን መቶ ይጐድለዋል ። ይህ ቢፈጸም ሰው እንደሆን ለማጠየቅ ባህያ መቀመጡ ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ፤ ትንቢት አጠፍዕ ሠረገላ እም ኤፍሬም ወአፍራሰ እምይሁዳ ተብሎ ተነግሯል።

ምሳሌም ቀድሞ አባቶቹ ነቢያት ዘመነ ጸብእ የሆነ እንደ ሆነ በፈረስ ተቀምጠው ዘገር ነጥቀው ይታያሉ ዘመነ ሰላም የሆነ እንደሆነ ባህያ ተቀምጠው መነሳንስ ይዘው ይታያሉና ዘመነ ሰላም ደረሰ ሲል ትንቢቱን ባወቀ አናግሯል ምሳሌውንም አንድ ባወቀ አስመስሏል ምሥጢሩ እንደምነው ቢሉ

ባህያ የተቀመጠ ሸሽቶ አያመልጥም አሳዶም አይዝም እሱም ካልሹኝ አልገኝም ከሹኝም አልታጣም ቢል ፥ አንድም እለ ከመ እንተ እድግ ነፍስቶሙ እንዲል ፥ በንጹሐን መሐይምናን አድሬባቸው እናራለሁ ሲል ፥ ዕድግት የእስራኤል ምሳሌ የሠረገላ ቀንበር መሸከም የለመደች እንደሆነች እስራኤልም ሕግ መጠበቅ ለምደዋልና ዕዋል የአሕዛብ ቀንበር መሸከም ያለመደች እንደሆነች አሕዛብም ሕግ መጠበቅ ያለመዱ ናቸውና ፥ አንድም ዕድግት የኦሪት ዕዋል የወንጌል ምሳሌ ፥ ዕድግት ቀንበር መሸከም የለመደች እንደሆነ ኦሪትም የተለመደች ሕግ ናትና ዕዋል ቀንበር መሸከም ያለመደች እንደሆነች ወንጌልም ያልተለመደች ሕግ ናትና ።

፰ ወዘይበዝኁ ሕዝብ ነጸፉ አልባሲሆሙ ውስተ ፍኖት ።

፰ የሚበዙት ሕዝብ ልብሳቸውን በጐዳና አነጠፉ ሐተታ ፥ ለንጉሥ ላንተ ለተቀመጥኽባት አህያ መሬት መርገጥ አይገባትም ሲሉ ፥ አንድም በኢዩ ልማድ ኤልሳዕ ከደቂቀ ነቢያት አንዱን ቀርነ ቅብዑን ይዘህ ሂደህ ኢዩን ቀብተህ አንግሠኸው ፈጥነህ ና ከሰው ጋራ አትጫወት ብሎ ላከው ። ቢሄድ ኢዩን ከባልንጀሮቹ ጋራ ሲጫወት ቢደባባይ ተቀምጦ አገኘው ብየ መልእክት አለው ። እምኔነኑ እምኀበ መኑ አለው ከኛን ነው ከሌላ ቢለው ኀቤከ መልአክ ካንተ ተልኬ መጥቻለሁ አለው ፥ ከአልፍኝ ይዞት ገባ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ቀባዕኩከ ትንግሥ ላዕለ ሕዝብየ እስራኤል ብሎ ቀብቶት ሩጦ ሄደ። ኋላ ኢዩ መጣ ምን አለህ ንገረን አሉት ። ኢትአምሩኑ ከመ በከ ይዋዕዕ ዝ ብእሲ ፥ ይህ ሰው ዋዛ ፈዛዛ እንዲናገር አታውቁምን አላቸው ። እውቀነ ንገረን አሉት ፥ ንገረንማ ካላችሁኝ ትነግሣለህ ብሎ ቀብቶኝ ሄደ አላቸው ። እኛስ ሌላ ምን እንሻለን ብለው እኩሌቶቹ አንጽፈዋል እኩሌቶቹ ጋርደዋልና በዚያ ልማድ ።

ወካልዓንሂ ይመትሩ አዕጹቀ እምዑፀው ወይነጽፉ ውስተ ፍኖት ።

ሌሎችም ቅጠል እየቆረጡ በመንገድ ያነጥፉ ነበር ሐተታ ፥ ሰሌን ነው ያሉ እንደሆነ አብርሃም ይስሐቅን ይስሐቅ ያዕቆብን በወለዱ ጊዜ ፥ እሥራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ፥ ዮዲት ሆሎፎርኒስን በገደለች ጊዜ ፥ ሰሌን ቆርጠው ይዘው አመስግነዋልና በዚያ ልማድ ። አንድም ሰሌን እሾህም ነው ትእምርተ ኃይል ትእምርተ መዊእ አለህ ሲሉ ፥ እሬት አይበላውም ለብልዐ ይተወዋል ። ባሕርይህ አይመረመርም ሲሉ ትምር ነው ያሉ እንደሆነ ትምር ልዑል ነው ፥ ልዑል ባሕርይ ነህ ሲሉ ፍሬው አንድ ነው ። ዋሕድ ባሕርይ ነህ ሲሉ ፍሬው በእሾህ የተከበበ ነው ባሕርይህ አይመረመርም ሲሉ ዘይት ነው ያሉ እንደሆነ ዘይት ጽኑዕ ነው ጽኑዓ ባሕርይ ነህ ሲሉ ፥ ብሩህ ነው ብሩሃ ባሕርይ ነህ ሲሉ ፥ መሥዋዕት ነው ። መሥዋዕት ትሆናለህ ሲሉ ።

፱ ወሕዝብሰ እለ ይመርሁ ወእለኒ ይተልዉ ይጸርኁ ወይብሉ ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት ። መዝ፡ ፻፲፯ ፡ ፳፮ ። ማር ፡ ፲፩ ፡ ፱ ፡ ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፴፰ ።

፱ በፊት በኋላ ያሉ ሕዝቡም ለዳዊት ልጅ መድኃኒት መባል ይገባዋል ። አሉ ።

ሐተታ ፥ ይተልዉ አዕሩግ ይመርሑ ሕፃናት ይተልዉ ሕፃናት ይመርሑ አዕሩግ ይተልዉ ሐዋርያት ይመርሑ ነቢያት እልፍ ቅድሜሁ እልፍ ድኅሬሁ ። ጻድቃን በየማኑ ተነሳሕያን በፀጋሙ እኒህ ሁሉ ለዳዊት ልጅ መድኃኒት መባል ይገባዋል እያሉ አመስግነዋል ።

ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ።

በእግዚአብሔር ስም ማለት እግዚአብሔር ነኝ ብሎ እግዚአብሔር ባወጣለት ስም በስሙ እግዚአብሔር ፥ እግዚአብሔር ፥ መስክሮለት የ[illegible] እሱ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚያድል ነው አሉ ።

ሆሣዕና በአርያም ።

በሰማይ ያለ መድኃኒት ነው ።

፲ ወበዊኦ ኢየሩሳሌም ተሀውከት ኵላ ሀገር እንዘ ትብል መኑ ውእቱ ።

፲ በኢየሩሳሌም ከተማ በገባ ጊዜ ይህ ማነው ብላ ከተማዋ ተደነቀች የፊቱ ብርሃን ፀሐይን ቢበዘብዛት አይታ የሕፃናትን ምስጋና ሰምታ ።

፲፩ ወይቤሉ ሕዝብ ዝንቱ ውእቱ ኢየሱስ ዘእምናዝሬት ዘገሊላ ። ማር ፲፩ ፡ ፲፭ ። ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፵፭ ። ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ።

፲፩ ሕዝቡ የገሊላ ክፍል በምትሆን በናዝሬት ያደገ ኢየሱስ ነው አሉ ።

ዘኪሙ ሰደዶሙ ኢየሱስ ለእለ ያረኩሱ ቤተ መቅደስ ።

፲፪ ወቦአ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ቤተ መቅደስ ።

፲፪ ጌታ ከቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ።

ወሰደደ ኵሎ እለ ይሠይጡ ወይሣየጡ ውስተ ቤተ መቅደስ የሚሸጡትን ሁሉ አስወጣ ማለት ገበያውን ፈታ ።

ወገፍትዓ ማዕዳቲሆሙ ለመወልጣን ።

ዙፋን ለወርቅ ወርቁን ለብር የሚለውጡበትን ሰፍራቸውን አፈረሰባቸው ።

ወመናብርቲሆሙ ለእለ ይሠይጡ ርግበ [illegible] ርግብ የሚሸጡትንም ወንበራቸውን ገለበጠባቸው ።

ሐተታ ፡ የከተማ ቅሬ በወንበር ተቀምጣ ዶሮ አን ድትሸጥ አንሱ ቋንጤ ወምበር አላቸው ከዚያው ላይ ሁነው ርግብ ይሸጣሉና ።

፲፯ ወይቤሎሙ ጽሑፍ ቤትየሰ ቤተ ጸሎት ይሰመይ ። ኢሳ ፶፮ ፡ ፯ ፡ ኤር ፡ ፯ ፡ ፲፩ ፡ ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፵፮ ።

፲፯ ቤቴ ቤተ መቅደስ የጸሎት ቤት ይባላል የሚል ጽሑፍ አለ ። ወአንትሙሰ ረሰይክምዎ በአተ ፈያት ወሰረቅት ።

እናንተ ግን የሌባ ዋሻ የወንበዴ ጋሻ አደረጋችሁት። ዋሻ ከሆነ ግን የተሰረቀውን የተቀማውን ይሸሽጉበታል ይልሙሙበታልና እንዲህ አለ ። አንድም ዋሻው የሌባው ነው ያሉ እንደሆነ ሁለቱን ቅጽር ወደ ውስጥ አንዱን ቅጽር ወደ ውጭ አድርገው ዋሻ አድርገዋል ስለምን ቢሉ ቀረጥ ፈርተው ።

ዋሻ ገብተው አይተርፏቸውም ቢሉ አይ **ተርፏቸውም** እንደ **ሕጋቸው** ይገዟቸዋል እያወጡ **ይሸጣሉ አንድም** ድል ገበያ ሲሆን እጅም ያስፈራ ነበርና ዘግቶ ለመዋጋት ። የካህናት ክልክል መስክ አለ ከካህናት አንዱ የሚያስወግሽ ልብስ ለብሶ ወደ ከብቱ ሂዶ ይቆማል ወግሽቶ ይገባል አውጥቼ ልውሰድ ያለ እንደሆነ ከል የገባ አይነጣ ቤተ መቅ ደስ የገባ ኢይወጣ እያሉ በምክንያት ያስቀሩባቸዋልና እንዲህ አለ ። ገበያው የካህናቱ ነው ያሉ እንደሆነ ካምቢተኛው ቆመ ብእሲ አድርገውታል ። ለመሥ ዋዕት ይሆናል ብሎ የሰባውን ከሩቅ አገር ነድቶ ይዞ ይመጣል ፡ ከመንገድ ይከሳበታል እመቦ ዘቦ ዝክር ሥናይ ዘያበውእ በግዓ ንውረ ርጉም ውእቱ ትሳለች እሪት ይኸን ለምን አመጣኸው ይሉታል እኔስ የሰባውን ነበር ያመጣሁት ከመንገድ ከሳብኝ እንጂ ይላል ቅንነቱማ ካለ የሰባ የኛ አለ ባንድ ሁለት ለውጠህ አትሠዋም ይሉታል እሺ ብሎ ለውጦ ይሠዋልና ።

ቀይ ወርቅ ያጣ እንደሆነ ነጭ ወርቅ ይዞ ይመጣል ፡ ለምን ይኸን አመጣህ ይሉታል ቀይ ወርቅ ባጣ ነው እንጂ ይላል ቅንነቱማ ካለ ከኛ ቀይ ወርቅ አለ ባንድ ሁለት አትሰጥም ይሉታል እንዲህ እያሉ ሁለተኛ ይቀበሉታልና እንዲህ አለ።

፲፬ ወመጽኡ ኀቤሁ ዕውራን ወሐንካሳን በቤተ መቅደስ ።

፲፬ ጌታ በቤተ መቅደስ ሳለ ዕውራን ሐንካሳን መጡ ።

ወአሕየዎሙ ።

አዳናቸው ።

፲፭ ወሶበ ርእዩ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት መን ክረ ዘገብረ ወደቂቅኒ እንዘ ይጸርኁ በቤተ መቅ ደስ ወይብሉ ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት ።

፲፭ ሊቃነ ካህናት ጸሐፍትም ያደረገውን ታም ራት አይተው ለዳዊት ልጅ መድኃኒት መባል ይገ ባዋል ብለው ሲያመሰግኑ የሕፃናቱንም ምስጋና ሰምተው ኢሐወዞሙ ።

ደስ አላሰኛቸውም ። ኢሐወዘኒ ሶበ ሞቁ ፤ ኢሐወዘኒ ስዕማኤ አፉከሙ እንዲል ።

፲፮ አሳ አንጐርጐሩ ።

አዘኑ እንጂ ።

ወይቤልዎ ኢትሰምዕኑ ዘይብሉ ፤

እሉ ሕፃናት ። መዝ ፡ ፰ ፡ ፪ ።

፲፮ እሊህ ሕፃናት የሚሉትን አትሰማምን አሉት ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እወ ።

እምን እስማለሁ ይገባኛል ብየ ነው እንጂ አላቸው ፡ አልቦኑ አመ አንበብክሙ ዘይቤ እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ ።

እንዲገባኝማ ለማጠየቅ ከልጆች ከሕፃናት አፍ ምሥጋና አዘጋጅ ያለውን የተመለከታችሁበት ጊዜ የለም አልተመለከታችሁም አላቸው ። ሐተታ ፡ ደቂቅ የመንፈቅ ያመት ሕፃናት ያመት ከመን ፈቅ የሁለት ዓመት ። አንድም ደቂቅ ያርባ የሰማንያ ቀን ሕፃናት የመንፈቅ ያመት ናቸው ። ለነዚህ መሥዋዕት ሊሰውላቸው ፅኑሰ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዘውላቸው ወጥተዋል ሕፃናትም እናት አባታቸውን ተከትለው ወጥተዋል እዕ ባን ሲያመሰግኑ አይተው ከናቶቻቸው ትከሻ እየወረዱ ሰሌን እየቆረጡ ይዘው አመሰግነዋል ።

፲፯ ወኀደጎሙ ወወፅአ አፍአ እም ሀገር ወቦአ ቢታንያ ወቤተ ሀየ ።

፲፯ ትቷቸው ከከተማ ወጥቶ ቢታንያ ገብቶ አደረ ።

በእንተ በለስ ዘተረግመት ።

፲፰ ወጸቢሖ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ የዓርግ ሀገረ ርኅበ ፡

፲፰ ማለዳ ወደ ከተማ ሲወጣ ተራበ

፲፱ ወርእየ ዕፀ በለስ በፍናት ፡ ማር ፲፩ ፡ ፲፫ ።

፲፱ በመንገድ ዕፀ በለስን አየ ፡

ወሖረ ኀቤሃ ይንሣእ ፍሬ እምኔሃ ።

ፍሬ ባገኝባት ብሎ ወደሷ ሄደ ወአልቦ ዘረከበ ውስቴታ ዘእንበለ ቆጽል ባሕቲቱ ።

ከቅጠል ብቻ በቀር ፍሬ አላገኘባትም ።

ወይቤላ ኢይኩን ፍሬ እምውስቴትኪ ለዓለም ፡ እንግዲህ ወዲህ ለዘላለም ፍሬ አይገኝብሽ ብሎ ረገማት ፡ ወየብሰት በጊዜሃ ይእቲ በለስ ያን ጊዜ ፈጥና እንድም በምትለመልምበት ጊዜ ደረቀች

ሐተታ ፡ በማርቆስ እስመ ኢኮነ ጊዜሁ ለበለስ ይላል ሊቁም ኢስመ ሙዋዕለ ክረምት ውእቱ ይላል እንደሌለ ያውቅ የለም ቢሉ አንዳንድ በዠረ በለስ አይታጣም ብሎ ያው ቅሉ እንደሌለ ያውቅ የለም

ቢሉ አላዋቂ ሥጋን እንደ ተዋሐደ ለማጠየቅ ፡ እኮ ኢያእምሮ ኀቡአተ እላ ከመ የሀብ ሪመካነ ለጥንተ ትስብእቱ ዘኢየአምሮ ኀቡአተ እንዲል ፡ አንድም አውቃለሁ ብሎ ሥራውን አይተውምና ቢያው ሥራውን ለመሥራት ፡ አንድም ወጸቢሖ ብለህ መልስ ሰው በሆነ ጊዜ ሰው ሁኖ ሲያስተምር ከሰው ፍቅር ተራበ ወርአየ ዕፀ በለስ እሥራኤልን በኢየሩሳሌም አገኘ በለስ ዘይቤ ቤተ እሥራኤል እሙንቱ እንዲል ወሖረ ሀቤሃ ፡ ሃይማኖት ምግባር ባገኝባቸው ብሎ ሄደ አላገኘባቸውም ዘእንበለ ቆጽል ባሕቲቱ እሥራኤል ከመባል በቀር እሥራኤል መባል ብቻ ነው እንጂ ወይቤላ ኢይኩን እንከ ፍሬ ደግ ሰው እንዳ ይገኝብሽ ብሎ ረገማት ወየብሰት ፡ ያን ጊዜ ደግ ሰው ጠፋ ። ምነው እስጢፋኖስ ጳውሎስ ኤጲፋን ዮስ ፲፬ እልፍ ካራት ሽህ ሰማዕታት ሕፃናት የተ ገኙ ከእሥራኤል አይደለም ቢሉ ከኒህ በቀር ቢል ነው አንድም መልስ አሪትን በዚህ ዓለም ሰፍና አገኛት ፡ ወሖረ ኀቤሃ ፡ ፈጻሚ ሕግ ተባለ ። ወአልቦ ዘረከበ ዘእንበለ ቆጽል ፡ ፈጻሚ ሕግ ከመባል በቀር ድኅነትን አላደረገባትም ።

ወይቤላ ኢይኩን ፍሬ ባንቺ ድኅነት አይደረግ አላት ። ወየብሰት ፡ አሪት ፈጥና ዐረፈች ። አንድም ወርአየ ዕፀ በለስ ብለህ መልስ የበለስ ቅጠል ሰፊ እንደሆነ ኃጢአትን በዚህ ዓለም ሰፍና አገኛት ። አንድም በለስ ሲበሉት ያጣፍጣል ቆይቶ ይኮመጥጣል ። ኃጢአትም ሲሠሩት ደስ ያሰኛል ኋላ ያሳዝናልና ፡ ወሖረ ኀቤሃ ኃጥአ ተባለ ወአልቦ ዘረከበ ፡ ኃጥእ ተመባል በቀር ኃጢአት አልሠራም ። ወይቤላ ኢይኩን እንከ ፍሬ ፡ ባንቺ ፀመጣ ፍዳ የሚ ያዝ አይኑር አላት ወየብሰት ፡ ኃጢአትም ፈጥና ጠፋች ። በእንጻረ በለስ ረገማ ለኃጢአት እንዲል።

በእንተ ትውክልት ኀበ እግዚአብሔር ።

፳ ወርእዮሙ አርዳኢሁ አንከሩ ወይቤሉ እፎ በጊዜሃ የብሰት በለስ ። ማር ፲፩ ፡ ፳ ።

፳ ደቀ መዛሙርቱ አይተው በምትሰመልም በት ጊዜ ፈጥና እንደምን ደረቀች ብለው አደነቁ ።

፳፩ ወአውሥአ ወይቤሎሙ እማን እብለክሙ ከመ እመ ብክሙ ሃይማኖት ወኢትናፍቁ እኮ ከመ ዕፀ ባሕቲቶ ዘትገብሩ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ።

፳፩ ሃይማኖት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩ ዕን ጨት ብቻ አድርቃችሁ አትቀሩም ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ።
አላ ለዝንቱኒ ደብር እመ ትብልዎ ፍልስ ወተ ወረው ውስተ ባሕር ይትገበር ለክሙ ። ይኸንም ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ከባሕር ግባ ብትሉት ይደረ ግላችኋል እንጂ ታሪክ እንዳለፈው ም፡ ፲፯ ፡ ቍ፡ ፭ ።

፳፪ ወኵሎ ዘሰአልክሙ በጸሎት እንዘ ትት እመኑ ትነሥኡ ፡

ማቴ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ ማር ፡ ፲፩ ፡ ፳፬ ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮፡፳፫

፳፪ በሃይማኖት ጸንታችሁ የለመናችሁትን ሁሉ ታገኛላችሁ ።

ዘከመ ተስእሎሙ እግዚእ ኢየሱስ በእንተ ጥምቀተ ዮሐንስ

፳፫ ወበዊአ ቤተ መቅደስ እንዘ ይሜህር መጽኡ ኀቤሁ ሊቃነ ካህናት ወመላህቅተ ሕዝብ ወይቤልዎ በመባሕተ መኑ ትገብር ዘንተ ።
ማር ፲፩ ፡ ፳፰ ። ሉቃ ፡ ፳፡፪ ።

፳፫ ከቤተ መቅደስ ገብቶ ሲያስተምር ሊቃነ ካህናት የሕዝቡም አለቆች መጥተው ይህን የምታ ደርግ ከምድራውያን ነገሥታት ከሌዋውያን ካህ ናት ወገን ያይደለህ ገበያውን መፍታትህ ማን አስ ናብቶህ ነው ። ወመኑ ወሀበከ ዘንተ ሥልጣነ በማን ሥልጣን ነው አሉት ።

፳፬ ወአውሥአ ። መለሰ ወይቤሎሙ እሴ አለክሙ እነሂ አሐተ ቃለ ።

፳፬ እኔም አንድ ነገር እጠይቃችኋለሁ አላ ቸው ። ሐተታ ቢጠይቁት መመለስ ነው እንጂ መጠ የቅ ይገባልን ቢሉ ቅድሚያ አለኝ ቢል ነው ምሳሌ በግዕን ጠይቋቸው አልመለሱለትም ነበርና ። አንድም እንደ ምላሽ ያለ ጥያቄ ነው ። እምከመ ነገርክሙኒ እነሂ እየድዓክሙ በአይ ሥልጣን እገ ብር ዘንተ ።
የነገራችሁኝ እንደሆነ ገበያውን የምፈታ በማንም ሥልጣን እንደሆነ እኔም እነግራችኋለሁ ።

፳፭ ጥምቀቱ ለዮሐንስ እምአይቴ ውእቱ ፡
፳፭ የዮሐንስ ጥምቀት ከወዴት ነው ማለት ዮሐንስ ማስተማሩ በማን ፈቃድ ነው ።
እምሰማይኑ ወሚመ እምሰብእ ከሰማይ ነውን ማለት በእግዚአብሔር ፈቃድ ነውን ፡ ወይስ በሰው ፈቃድ ነው አላቸው ወሐለዩ በበይናቲሆሙ ወይቤሉ ። አርስበርሳቸው እንዲህ አሉ ።

፳፮ እመ ንብሎ እምሰማይ ይብለነ በእፎ ዘኢ አመንክምዎ ፡ ማቴ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ ።

፳፮ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብንለው ምነው ያላመናችሁበት ይለናል ።
ወእመ ንብሎ እምሰብእ ንፈርሆሙ ለሕዝብ ፡
በሰው ፈቃድ ነው ብንለው ሕዝቡን እንፈራለን ። እስመ ከመ ነቢይ ይሬስይዎ ለዮሐንስ በኀቤሆሙ ዮሐንስን እንደ አባት ያከብሩታል እንደ መምህር ያፍሩታልና ወእውሥኡ መሰሉ ።

፳፯ ወይቤልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ኢነአምር።
፳፯ አናውቅም አሉት ።
እነሂ ኢያየድዓክሙ በአይ ሥልጣን እገብር ዘንተ።
ገበያውን በማንም ሥልጣን እንደ ፈታሁት እኔም አልነግራችሁም አላቸው ።
፳፰ ወምንተ ትብሉ ።

፳፰ ምን ትፈርዳላችሁ ። ብእሲ ቦቱ ፪ቱ ደቂቅ እንዃው ፤ ላንድ ሰው ሁለት ልጆች አሉት ።
ወይቤሎ ለቀዳማዊ ሑር ወወልድየ ተቀነይ ዮም ውስተ ዐፀደ ወይንየ ።
ታላቁን ልጁን ልጄ ዛሬ ሂደህ ወይን ጠብቅ አለው

፳፱ ወአውሥአ ወይቤ እሆ እግዚእየ ።
እሺ አለው ።
ወኢሖረ ።
ሳይሄድ ቀረ ።

፴ ወለካልኡኒ ይቤሎ ከማሁ ፤
፴ ታናሹን ሂደህ ወይኑን ጠብቅ አለው ።
ወይቤ እንብየ ።
አይቻለኝም አለ ።
ወእምድኅረዝ ነስሐ ወሖረ ።
ከዚህ በኋላ ያባቱን ትእዛዝ አፈረስሁን ብሎ ሄደ ።

፴፩ መኑ እንከ እም፪ሆሙ ዘገብረ ፈቃደ አቡሁ ።
፴፩ እሄዳለሁ ብሎ ከቀረውና አልሄድም ብሎ ከሄደው ያባቱን ፈቃድ የፈጸመ ማነው አላቸው ።
ወይቤልዎ ደኃራዊ ።
ታናሹ ነዋ ታላቁማ ዘበተበት እንጂ አደረገስትን አሉት ።

ሐተታ ፤ ታላቅ ልጅ የተባሉ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ። ታናሽ ልጅ የተባሉ ኃጥአን መጸብሐን ናቸው ። እሄዳለሁ ብሎ እንደ ቀረ አሪትን ተቀብለው በወንጌል ሳያምኑ ቀርተዋል ። አልሄድም ብሎ እንደሄደ ኃጥአን መጸብሐንም ሕጉን ካፈረሱ በኋላ በወንጌል አምነዋልና ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አማን እብለክሙ ከመ መጸብሐን ወዘማውያን ይቀድሙክሙ በዊአ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
ኃጥአን መጸብሐን ቀድመዋችሁ መንግሥተ ሰማይ ይገባሉ ብየ እንዲገቡ በውነት እነግራችኋለሁ ።
መከተሉስ አሰና እንዲህ አስ ቢሉ ቢያምኑ እንዲ ያገባቸው ለማጠየቅ ፤

፴፪ እስመ መጽአ ኀቤክሙ ዮሐንስ በፍኖተ ጽድቅ ወኢ አመንክምዎ ።
፴፪ ዮሐንስ ወንጌልን ቢያስተምር አንቀበልህም ብላችሁታልና ወመጸብሐንስ ወዘማውያን አምንዎ ።
ኃጥአን መጸብሐን ግን አምነውታልና ።
ወአንትሙስ ርኢክሙሂ ኢነሳሕክሙ ።
እናንተ ግን አይታችሁ አላመናችሁም ።
ድኅረ ለአሚን ቦቱ ።
ኋላ ለማመን ፤ አንድም ድኅረ ከመ ትእመኑ ቦቱ ኋላ ታምኑበት ዘንድ ። አንድም ነሳሕክሙ ድኅሬሁ ለአሚን ከማመን ወደኋላ አፈገፈጋችሁ ። አንድም ድኅሬሁ ፤ ኋላ ታምኑበታላችሁን ። ድኅረሰ ተአምኑ ቦቱ ኋላ ግን ታምኑበታላችሁ አርድኦ ርእይ ታመጽአ አሚን ፤ እንዲል ፤ እሮ ኮነ ወልደ ዕጓለ እመ ሕያው ይሉታልና ።

በእንተ አኩያን ገባዕት ።

፴፫ ወይቤሎሙ ካልዕተ ምሳሌ ስምዑ ።
ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፩ ፡ ኤር ፡ ፪ ፡ ፳፩ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፩ ፡ ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፱ ።

፴፫ ፪ኛ ምሳሌ ስሙ ፤ ብእሲ በዓለ ቤት ተከለ ዐጸደ ወይን ። ባለቤት ወይን ተከለ ፡ ዐጸደ ወይን አፍለስከ እምግብጽ እንዲል ፤ ዐጸደ ወይን ሐረገ ወይን ጕንደ ወይን ምንዳደ ወይን ይላል አብነት ።
ወገብረ ሎቱ ጸቆነ ።
ቅጽር ቀጠረለት ።
ወአክረየ ሎቱ ምክያደ ።
የዘቢብ ማስጫ ውድማ አበጀለት ።
ወሐነጸ ማኅፈደ ።
ለጠባቂ ግንብ ሠራ ።
ወሤመ ዓቀብተ ።
ጠባቂ ሾመ ።
ወወሀቦሙ ለዓቀብት ወነገደ ።
ጠባቂ ሹሞ ሄደ ።

፴፬ ወአመ በጽሐ ጊዜ ፍሬሁ ፈነወ አግብርቲሁ ኀበ ዓቀብቱ ወይን ፤
፴፬ የሚያፈራበት ጊዜ ቢደርስ ብላቴኖቹን ከጠባቆች ላከ ።
ከመ ያምጽኡ ሎቱ እምፍሬ ወይኑ ።
ከወይኑ ፍሬ ያመጡለት ዘንድ አምጡ ብሎ ፤
፴፭ ወአኀዝዎሙ ዓቀብት ለአግብርቲሁ ።
፴፭ ጠባቆች ብላቴኖችን ይዘው ቦ ዘቀተሉ ።
የገደሉት አለ ።
ወቦ ዘወገሩ ።
በደንጊያ የመቱት አለ ።
ወቦ ዘቀሠፉ ።
የገረፉት አለ ።
፴፮ ወእምዝ ፈነወ ካልዓነ አግብርተ ዘይበዝኁ እምቀደምት ።
፴፮ ከዚህ በኋላ ከቀደሙት የሚበዙ ሌሎች ብላቴኖች ላከ ። ወኪያሆሙኒ ከማሁ ረሰይዎሙ ። እላቸውንም እንደዚሁ አደረጓቸው የገደሉት በደንጊያ የመቱት የገረፉት አለ ።
፴፯ ወድኅረ ፈነወ ኀቤሆሙ ወልዶ እንዘ ይብል የኀፍርዎ ለወልድየሰ ።
፴፯ ከዚህ በኋላ ልጄንስ ቢሆን ያከብሩታል ባይሆንም ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከ ።
፴፰ ወሶበ ርእይዎ ዓቀብት ለወልዱ ወይቤሉ በበይናቲሆሙ ነዋ ዝንቱ ውእቱ ወራሲሁ ንዑ ንቅትሎ ወንርከብ ርስቶ ። ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፬ ፡ ፳፯ ፡ ፩ ።

፴፰ ጠባቆች ባዩት ጊዜ ርስቱ ይገባኛል የሚል እነሆ ይህ ነው እሱን ገድለን ርስቱን እጅ እናድርግ አሉ ፤

፴፱ ወነሥእዎ ወአውፅእዎ አፍአ እምዓጸደ ወይን ወቀተልዎ ። ዮሐ ፡ ፲፩ ፡ ፶፫ ።

፴፱ ይዘው ከወይኑ ቦታ አውጥተው ገደሉት የሰው ደም ተክል የደርቃል ይባላልና ።

፵ ወሶበ መጽአ በዓለ ዓጸደ ወይን ምንተ ይሬስዮሙ ለእሉ ዓቀብት ።

፵ የወይኑ ባለቤት በመጣ ጊዜ ምን ያደርጋቸዋል እነዚህን ጠባቆች አላቸው ።
፵፩ ወይቤልዎ በእኪት ለእኩያን ያጠፍዖሙ
፵፩ እንደመሰለባቸው ያወቁት እንዲህ የሚያደርግ የለም ብለዋል ፤ ያላወቁት ግን ይሙት በቃ ፈርዶ ይገላቸዋል አሉ ፤
ወወይናሂ ይሁብ ለካልዓን ዓቀብት ።
ወይኑንም ለሌሎች ሰዎች ያስጠብቃል ።
ለእለ ይሁብዎ ፍሬሁ በበጊዜሁ ፍሬውን በየጊዜው ለሚያቀርቡለት ።
ወበበአግዋሊሁ ።
በየዘለላው ፤ ካንዱ ዘለላ ቀይ ጥቁር ነጭ ያፈራልና እንድም ብእሲ በዓለ ቤት ብለህ መልስ ፤ እምጼኤ ዓለማት ፈጣሬ ዓለማት አብ ሕገ ኦሪትን ሠራ ፤ ወገብረ ሎቱ ጸቆነ ፤ በኦሪት ረድኤት እንዲገኝ ማድረጉን መናገር ነው ፤ ወአክረየ ምሥዋዓ ብርትን ፤ ወሐነጸ ቤተ መቅደስን ሠራ ፤ እንድም ወአክረየ ልቡናን ፤ ወሐነጸ ማኅፈደ ተልዕሎተ ትንቢትን ፤ እንድም እምጼኤ ዓለማት ፈጣሬ ዓለማት አብ በልጁ ህልው ሁኖ ወንጌልን ሠራ ወገብረ ሎቱ፤ በወንጌል ልጅነት እንዲገኝ አደረገ ።

ወአክረየ ፤ ንዋየ ቅድሳትን ፤ ወሐነጸ ቤተ ክርስቲያንን ሠራ ። እንድም ወአክረየ ሰፍሐ አእምሮን ወሐነጸ ተልዕሎተ ፤ ሃይማኖትን ሠራ ፤ ወወሀቦሙ ለዓቀብት ። ጠብቁ ብሎ ሕግ መሥራቱን መናገር ነው ወአመ በጽሐ ። ሃይማኖት የሚይዙበት ምግባር የሚሠሩበት ጊዜ ቢደርስ ፈነወ አግብርቲሁ ፤ ሃይማኖት ምግባር ያሠሩለት ዘንድ ዓበይተ ነቢያትን ላከ ፤ ወነሥእዎሙ ሕግ መጠበቅ የሚገባቸው ሕዝቡ ዓበይተ ነቢያትን ደቂቀ ነቢያትን ይዘው ቦ ዘቀተሉ ፤ የገደሉት አሉ እነ ኢሳይያስን ወቦ ዘወገሩ እነኤርምያስን ። ወቦ ዘቀሠፉ ፤ እለ አሞጽን ሠያጤ በለስ ብለው ገርፈውታል ።
ወእምዝ ፈነወ ከዚህ በኋላ ከዐበይተ ነቢያት የሚበዙ ደቂቀ ነቢያትን አስተምሩ ብሎ ላከ ። ወኪያሆሙኒ ከማሁ እሳቸውንም እንደነዚያ አደረጓቸው ። ወእምዝ ፈነወ ከነዚህ ሁሉ በኋላ ልጁን በሥጋ ላከ ።

ልጄንስ ቢሆን ያከብሩታል ባይሆን ያፍሩታል ብሎ ፤ ወሶበ ርእይዎ ፤ ሕግ መጠበቅ የሚገባቸው ሕዝቡ ሰው ሁኖ ባዩት ጊዜ መምህርነት ይገባኛል የሚል እነሆ መጣ ንዑ ንቅትሎ እሱን ገድለን መምህርነቱን ገንዘብ እናድርግ አሉ ። ወአውፅእዎ ከከተማው አፍአ አውጥተው በቀራንዮ ሰቅለው ገደሉት ። እንድም ሕግ መጠበቅ ከሚገባው ከልቡናቸው አውጥተው ጠልተው ተመቅኝተው ሰቅለው ገደሉት ።

ወሶበ መጽአ ምንተ ይሬስዮሙ ሲል ነው ። የሕጉ ባለቤት ጌታ በመጣ ጊዜ ምን ያደርጋችኋል አላቸው ፤ ወይቤልዎ በእኩይ ለእኩያን ይቀትሎሙ ። ፈርዶ ያጠፋቸዋል አሉት ። ወወይናሂ ይሁብ ፤ ሕጉንም ለሌሎች ያስጠብቃል ። ለእለ ይሁብዎ ።

በዓሉን በየጊዜው ለሚያከብሩ መጻለት ሰዊት ፋሲካ ነው ። ወበበአግዋሊሁ በየአገባቡ ።

፵፪ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አልቦሁ አመ አንበብክሙ ውስተ መጻሕፍት እብን እንተ መነንዋ ነደቅት ይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማዕዘንት ። መዝ ፻፲፯፡፳፪ ። ግብ፡፬፡፲፩። ሮሜ፡፱፡፴፫ ። ፩ጴጥ፡፪፡፯ ።

፵፪ እናጢዎች የናቋት ደንጊያ የማዕዘን መሰብሰቢያ ሆነች ፤ እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ ።
ይህች በእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነች ።
ወነካር ይእቲ ለአዕይንቲነ ።

ለዓይነ ልቡናችን ድንቅ ናት ብሎ መጽሐፍ የተናገረውን የተመለከታችሁበት ጊዜ የለምን አላቸው ። እንድም እንተ መነንዋ ብለህ መልስ አሕዛብ የናቋት ኦሪት በ፬ ማዕዘን መከበሪያ መጽደቂያ ሆነች ። እምኀበ እግዚአብሔር ። መናቋም መከበሪያ መጽደቂያ መሆንዋም በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። ነቋም እግዚአብሔር አብ ነው ወነካር ለዓይነ ልቡናችን ድንቅ ናት ። እንድም እብን እንተ መነንዋ አሕዛብ የናቁት ዘሩባቤል ንጉሠ ነገሥት ሆነ ። መናቁም ንጉሠ ነገሥት ። መሆኑም በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ወመንክር በል ለዓይነ ልቡናችን ድንቅ ነው ወያዕቆብስ ያስተኤሬ ንጉሠ እንዲል ሁለቱ ካሥሩ ነገድ ከተለዩ በኋላ አንድ አድርጎ ነግሧልና ። እንድም እብን እንተ መነንዋ ሐና ቀያፋ የካዱት ክርስቶስ ንጉሠ ነገሥት በዠረ ምእመናን ሆነ ሐተታ ። ነደቅት አላቸው የሰውን ልቡና በትምህርት እናንጻለን ይላሉና እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ።

መናቁም በዠረ ምእመናን ንጉሠ ነገሥት መሆኑም በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ነቁም እግዚአብሔር ነው ወመንክር ፤ ለዓይነ ልቡናችን ድንቅ ነው ። እንድም እብን እንተ መነንዋ ፤ ጸሐፍት ፈሪሳውያን የናቋት ወንጌል ፤ በአራት ማዕዘን መከበሪያ መጽደቂያ ሆነች ፤ እምኀበ እግዚአብሔር ። መናቋም መከበሪያ መጽደቂያ መሆንዋም በእግዚአብ

ሔር ፈቃድ ነው ነቋም እግዚአብሔር ወልድ ነው። ወነካር ፣ ለዓይነ ልቡናችንም ድንቅ ናት ።

፵፫ ወበእንተዝ እብለክሙ ከመ ይነሥእዋ እምኔክሙ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ወይሁብዋ ለሕዝብ ዘይገብሩ ፍሬሃ ።

፵፫ ስለዚህ ነገር ማሰት አንቀበልም ስላላችሁ ወንጌልን ከናንተ ነሥተው ሥራቷን ለሚሠሩ ለሌሎች ሰዎች ያስጠብቋታል ብየ እነግራችኋለሁ ፣ እንዲሁም ባለ ጊዜ ክህነትንም መንግሥትንም ከላቸው እንዳላለፈባቸው ያጠይቃል ።

፵፬ ዘሰ ወድቀ ዲበ ይእቲ እብን ይትቀጠቀጥ ።

፵፬ ከደንጊያ ላይ የወደቀ ይሰበራል ወለዘሂ ወድቀት ዲቤሁ ተሐርያ የወደቀችበትም ይሰበራል ። ሐተታ ፣ በላይም ሆነ በታችም ሆነ ደንጊያ ሰባሪ ሰው ተሰባሪ ነው ። አንድም ዘሰ ወድቀ በዕለተ ዓርብ በጌታ በጠላትነት የተነሣበት አይሁዳዊ ፣ ይትቀጢቀጥ ፣ በታምራት ይጠፋል ወዘሂ ወድቀት ። ጌታ በታምራት የተነሣበት አይሁዳዊ የሐርያ ። በአርባ ዘመን በጥጦስ ይጠፋል ። አንድም ዘሰ ወድቀ ዲበ ዕብን በዕለተ ዓርብ በጌታ በጸላትነት የተነሣበት አይሁዳዊ በ፵ ዘመን በጥጦስ ይጠፋል ። ወላዘሂ ወድቀት ዲቤሁ ። ጌታ በአርባ ዘመን በጥጦስ በጠላትነት የተነሣበት አይሁዳዊ ተሐርያ ፣ በምጽአት ይጠፋል አንድም በመባሕተ መኑ ትገብር ዘንተ በማለት በጌታ በጠላትነት የተነሣ አይሁዳዊ ይትቀጠቀጥ ። ጥምቀቱ ለዮሐንስ እምኀበ አይቴ ባለው ይረታል ። ክርስቶስ ወልደ መኑ በማለት ጌታ በጠላትነት የተነሣበት አይሁዳዊ ዘለሊሁ ዳዊት እግዚእየ ይቤሎ በእፎ ይከውኖ ወልዶ ባለው ይረታል ።

፵፭ ወሰሚዖሙ ሊቃነ ካህናት ወፈሪሳውያን ምሳሌያቲሁ እንከሩ ወአእመሩ ከመ በእንቲአሆሙ ይብል ።

፵፭ ፈሪሳውያን ሊቃነ ካህናት ምሳሌውን ሰምተው አደነቁ በሳቸው እንደመሰለባቸው ዐወቁ

፵፮ ወፈቀዱ የእኃዝዎ ።

፵፮ ሊይዙት ወደዱ ።
ወፈርሁ ሕዝበ ።
ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ ።
እስመ ከመ ነቢይ ይሬእይዎ ሕዝቡ ጌታን እንዳባት ያከብሩታል እንደ መምህር ያፍሩታልና ።

በእንተ ምሳሌ ንጉሥ ዘገብረ ከብካበ ለወልዱ ።

ምዕራፍ ፳፪ ።

፩ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ዳግመ ወነገረ በምሳሌ ።

፩ ጌታ ሁለተኛ በምሳሌ ነገራቸው

፪ እንዘ ይብል ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብእሲ ንጉሠ ዘገብረ ከብካበ ለወልዱ ሉቃ ፲፬፡ ፪ ፲፮ ፡ ራዕ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ።

፪ መንግሥተ ሰማያት ሕገ ወንጌል ሕገ ወንጌል ተስፋ ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ለልጁ ሰርግ ያዘጋጀ ንጉሥን ትመስላለች ።

፫ ወፈነወ አግብርቲሁ ይጸውዕዎሙ ለእለ ተዓሠሩ ውስተ ከብካብ ።

፫ የታደሙትን ወደ ሰርግ ጥሯቸው ብሎ ብላቴኖቹን የላከን ወዓበዩ መጺአ ፣ አንመጣም ያሉትን ።

፬ ወዳግመ ፈነወ ካልዓነ አግብርተ ።
፬ ሁለተኛ ሌሎችን ላከ ።
እንዘ ይብል በልዎሙ ለእለ ዓሠርናሆሙ ።
ያደምናቸውን እንዲህ በሏቸው ብሎ ።
ናሁ ምሳሐየ አስተዳሎኩ እነሆ ሰርግ አዘጋጅቻለሁ
ወጠባሕኩ መጋዝዕትየ ወእስዋርየ ።
ሜል ገች አርጃለሁ ።
ወኵሉ ድልው ።
ሁሉ ተዘጋጅቷል ።
ንዑ ውስተ ከብካብየ ።
ወደ ሰርግ ኑ ብሎ ላከ ።

፭ ወእሙንቱሰ ተሐየዩ ወኃለፉ
፭ እሳቸው ግን ቸል ብለው ሄዱ
ቦ ዘሖረ ውስተ ገራኅቱ ፣
ወደ እርሻው የሄደ አለ ።
ወቦ ዘሖረ ውስተ ንግዱ ።
ወደ ንግዱ የሄደ አለ ።
ወቦ ዘሐረ ውስተ ዓጸደ ወይኑ
ወደ ወይን ጥበቃው የሄደ አለ

፮ ወእለ ተርፉ እኃዙ አግብርቲሁ ወቀተልዎሙ
፮ የቀሩት ግን ብላቴኖቹን ይዘው ገደሏቸው ።
ወኪያሁኒ እግዚእሙ ጸአሉ ። እሱንም ነቀፉት ።

፯ ወተምዓ ንጉሥ ወፈነወ ሐራሁ ይቅትልዎሙ ለእልክቱ ቀተልት ።

፯ ንጉሥ ተቆጥቶ ግደሏቸው ብሎ ጭፍራ ላከ
ወቀተልዎሙ ።
ገደሏቸው ።
ወሀገሮሙኒ አውዓዩ በእሳት ።
ሀገራቸውን አቃጠሉ ።

፰ ወእምዝ ይቤሎሙ ለአግብርቲሁ ከብካብየሰ ድልው ውእቱ ።

፰ ከዚህ በኋላ ለብላቴኖቹ ሰርጉስ ተዘጋጅቷል ።
ወባሕቱ ኢደለዎሙ ለእለ ዓሠርናሆሙ ።
ነገር ግን ላደምናቸው አላደላቸውም አላቸው ።

፱ ሑሩኬ እንከ ውስተ መራህብት ወአናቅጽ ወኵሎ ዘረከብክሙ ጸውዑ ሊተ ውስተ ከብካብ

፱ እኒያ አይሆንም ካሉ ወደ ዐደባባይ ወጥታችሁ ክፋውንም በጎውንም ጠርታችሁ ይዛችሁ ኑ አላቸው ።

፲ ወወፂአሙ አሙንቱ አግብርት ውስተ ፍናው አስተጋብኡ ኵሎ ዘረከቡ እኩያነ ወኄራነ

፲ ወደ ዐደባባይ ወጥተው ክፋውንም በጐውንም ያገኙትን ጠርተው ይዘው መጡ ።
ወመልአ ቤተ በዓል እምእለ ይረፍቁ ።
ከተቀመጡት የተነሣ የሰርግ ቤት መላ ።

፲፩ ወበዊአ ንጉሥ ይርአዮሙ ለእለ ይረፍቁ ረከበ በህየ ዘኢለብሰ ልብሰ መርዓ ።

፲፩ ንጉሥ ከሰርግ ቤት ገብተው የተቀመጡትን ሊያያቸው በገባ ጊዜ የሰርግ ልብስ ያለበሰ አንድ ሰው አገኘ ።

፲፪ ወይቤሎ አርክየ ለምንት ቦእከ ዝየ ዘኢለበስከ ልብሰ መርዓ ።

፲፪ ወዳጄ የሰርግ ልብስ ያለበስህ ከሰርግ ቤት ለምን ገባህ አለው ።
ወተፈጸመ ውእቱ ብእሲ ።
ያሰው ምላሽ አጣ ። ሐተታ ፡ ባጣ ቢቸግረኝ አይለውም ቢሉ ያኑ ከውኃ ባደረስከው ይለዋልና ።

፲፫ ወእምዝ አዘዞሙ ንጉሥ ለአግብርቲሁ ይእስርዎ እደዊሁ ወእገሪሁ ወያውፅእዎ ውስተ ጸናፌ ጽልመት ። ማቴ ፡ ፰ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ፡ ፫ ፡ ፵፪ ፡ ፳፭ ፡ ፴ ።

፲፫ ከዚህ በኋላ እጁን እግሩን አስራችሁ ወደ ጽኑ ጨለማ አውጡት ።
ኀበ ሀሎ ብካይ ወሐቅየ ስነን ።
ልቅሶ ጥርስ ቁርጥማት ወዳለበት ቦታ ብሎ ብላቴኖቹን አዘዛቸው ።

፲፬ እስመ ብዙኃን እሙንቱ ጽውዓን ።

፲፬ የተጠሩ የቀሩ ብዙ ናቸውና
ለምንት ቦእከ ዝየ ።
ወኅዳጣን ኅሩያን የተጠሩ የተመረጡ ጥቂት ናቸውና ፡ እሰሩ እደዊሁ ወእገሪሁ በል ። አንድም ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብለህ መልስ መንግሥተ ሰማይ አብ ለልጁ ሥጋዌን ያደረገ ንጉሥን ይመስላል ማለት እሱ ነው ። ወፈነወ አግብርቲሁ ፡ ትንቢት የተነገረላቸውን በአሪት ፡ ተሰፋ መስቀል የተነገረላቸውን በወንጌል ያሰምኑ ዘንድ አስተምሩ ብሎ ዓበይተ ነቢያትን ሐዋርያትን ላከ ። ወአበዩ ፡ እናምንም አሉ ። ወዳግመ ፈነወ ካልዓነ አግብርተ ፡ ለዓበይተ ነቢያት ካልዓን የሚሆኑ ደቂቀ ነቢያትን ለሐዋርያት ካልዓን የሚሆኑ ፸ አርድእትን ፡ ትንቢት የተነገረላቸውን በአሪት ተስፋ መስቀል የተነገረላቸውን በወንጌል አሳምኑ ብሎ ላከ ። ናሁ ምሳሀየ አስተዳሎኩ አሪትን ወንጌልን ሠርቻለሁ ፡ ወዘሎ ድልው ፡ በአሪት በወንጌል ጥቃቅኑ ደጋግ ታምራት ይደረጋል ። ንዑ ውስተ ከብካብየ ፡ በአራት በወንጌል እመኑ ብላችሁ አስተምሩ ብሎ ላካቸው ወእሙንቱሰ ተሐየዩ ፡ እላቸው ግን ቸል ብለው ሄደው ቦ ዘሐረ ውስተ ገራኅቱ ፡ እርሻችሁን ተው የምትል ሕግ አንሻም ብሎ ወደ እርሻው የሄደ አለ። ቦ ዘሐረ ውስተ ተግባሩ ፡ ንግዳችሁን ተው የምትል ሕግ አንሻም ብሎ ወደ ንግዱ የሔደ አለ ወቦ ዘሐረ ወስተ ዐጸደ ወይኑ ወይናችሁን ተው የምትል ሕግ አንሻም ብሎ ወደ ወይኑ ጥበቃው የሄደ አለ የቀሩት ግን ዓበይተ ነቢያትን ደቂቀ ነቢያትን ሐዋርያትን ፸ አርድእትን ይዘው ገደሏቸው ወኪያሁኒ ጸዓሉ ፡ እሱንም አሩቅ ብእሲ አሉት ። ወተምዓ ንጉሥ ፡ ጌታ ፈርዶ ነቢያትን በገደሉ ነገሥተ ፋርስን ሐዋርያትን ፸ አርድእትን በገደሉ ነገሥተ ሮምን አስነሥቶ አጠፋቸው ወሀገሮሙኒ አውዐዩ ፡ ሀገራቸውንም በእሳት አቃጠሉ።

ወእምዝ ይቤሎሙ ከብካብየስ ፡ ድልው ሕጉስ ተሠርቷል ወባሕቱ ኢደለዎሙ ለእለ ዓሠርናሆሙ ትንቢት ተስፋ መስቀል ላናገርንላቸው አልሆንላቸውም እንጂ ፡ ሑሩኬ ውስተ መራህብት ፡ በአራቱ መዓዝን ዙራችሁ አስተምራችሁ ያገኛችሁትን በአራት በወንጌል አሳምኑ ። ወወፂአሙ ውስተ ፍናው ባራቱ መዓዝን ዙረው አስተምረው በአሪት በወንጌል አሳመኑ ። እኩያነ ወኄራነ ፡ እኩያን አምነው ተጠምቀው ሥራ ያልሠሩ ናቸው ኄራን አምነው ተጠምቀው ሥራ የሠሩ ናቸው ። ወመልአ ቤተ በዓል እምእለ ይረፍቁ ፡ ከምእመናን ብዛት የተነሣ መንግሥተ ሰማያት መላች ። መምላትስ የለም ብዛታቸውን መናገር ነው እንጅ ወበዊአ ንጉሥ ያመኑትን የተጠመቁትን በተመራመራቸው ጊዜ ረከበ ብእሴ ዘኢለብሰ ልብሰ መርዓ ፡ አምኖ ተጠምቆ የክርስቲያን ሥራ ያልሠራ ሰው አገኘ ። ወይቤሎ አርክየ ለምንት ቦእከ ዘኢለበስከ ልብሰ መርዓ መፍቀሬ ሰብእ ነውና አርክየ ይለዋል ወዳጄ የክርስቲያን ሥራ ላትሠራ ለምን አመንኩ ተጠመቅሁ አልህ አለው ።

ወተፈጸመ ምላሽ አጣ ባሕርየ ደካማ ቢሆን ባይቻለኝ አይለውም ቢሉ ያኑ ከመምሀረ ንስሐሀ ባደረስኸው ይለዋልና ፡ ወእምዝ አዘዞሙ ንጉሥ ለአግብርቲሁ ። ከዚህ በኋላ መላእክትን ከመንግሥተ ሰማይ በአፍአ ጽኑ ፍዳ ወዳለበት ወደ ገሃነም አውጡት አላቸው ። እስመ ብዙኃን ጽውዓን፣ እንዳለፈው በል ።

፲፭ ወእምዝ ሖሩ ፈሪሳውያን ወተማከሩ ከመ ያስሕትዎ በቃሉ ማር ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ሉቃ ፳ ፡ ፳ ።

፲፭ ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን ሄደው በነገር ሊያስቱት መከሩ ።

በእንተ ዘከመ ይደሉ ውሂበ ጸባሕት ለቄሣር።

፲፮ ወፈነዉ ኀቤሁ አርዳኢሆሙ ምስለ ሰብአ ሄሮድስ ።

፲፮ ብላቴኖቻቸውን ከሄሮድስ ብላቴኖች ጋራ ላኩ በሀገር የሊቀ መጣኔ ወምበር እንዲኖር ያገር ምዝክር ሹማምት አሉና ፤ አንድም ብላቴኖቻቸውን የሄሮድስ ብላቴኖች ነን በሉ ብለው ላኩ ።
ወይቤልዎ ሊቅ ነአምር ከመ ራትዕ አንተ ።
መምህር ዐዋቂ ቅን እንደሆንህ እናውቃለን ።
ወበጽድቅ ትሜህር ፍኖተ እግዚአብሔር ።
በእውነት ወንጌልን እንድታስተምር ።
ወኢተሐውብ መነሂ ።
ማንንም ማንን እንዳትፈራ ፡ ወኢየኃዝነከ መኑሂ ይላል ማንም ማን እንዳያሳፍርህ ።
ወኢታደሉ ለገጸ ሰብእ ።
ፊት አይተህ እንዳታደላ እናውቃለን ።

፲፯ ንግረነኬ ዘይረትዕ ።

፲፯ የሚገባውን ንገረን ።
ይከውነነሁ ነሀብ ጸባሕተ ለንጉሥ ፤
ለቄሣር ግብር መስጠት ይገባናል ።
አው አልቦ ።
ወይም አይገባንም አሉት ፤ ሐተታ ፤ ይገባል ቢላቸው የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ይላል ለእግዚአብሔር የሚገባውን ለቄሣር ስጡ አለን ለማለት ፤ አይገባም ቢላቸው ከቄሣር ለማጣላት ነው ።
፲፰ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ እከዮሙ
፲፰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተንኮላቸውን ዐውቆባቸው ፤ ሚኖሙ ይላል አብነት እከዮሙ ማለት ነው ።
ወይቤሎሙ ምንተ ታሜክሩኒ አ መደልዋን ።
እናንተ ግብዞች ለምን ትፈትኑኛላችሁ ።
፲፱ አርእዩኒ አላደ ዲናሩ ።
፲፱ ቅርጹን አሳዩኝ አላቸው ።
ወአምጽኡ ሎቱ ዲናረ ።
፳ አመጡለት ።
፳ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ዘመኑ ዝንቱ መልክእ ወመጽሐፉ ።
ቅርጹ መጽሐፉ የማነው አላቸው ።
፳፩ ወይቤልዎ ዘቄሣር ።
የቄሣር ነው አሉት ። ሮሜ ፲፫ ፡ ፯ ።
፳፩ ወይቤሎሙ ዘቄሣር ሀቡ ለቄሣር ።
የቄሣርን ለቄሣር ስጡ ።
ወዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ አላቸው ምልአተ ንባብ ነው ። አንድም የንጉሥ የሆነ እንደሆነ ስመ ንጉሥ ይጸፍበታል ሥዕለ አንበሳ ይቀርጹበታልና የቄሣርን ለቄሣር ስጡ አለ የእግዚአብሔር የሆነ እንደሆነ ስመ አምላክ ይጻፍበታል ሥዕለ ኪሩብ ይቀረጽበታልና የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ አለ አንድም በተን ኳል መጥቶዋል መጠን እራኃ እድ ይላታል ብር የምታህል ናት ባንድ ወገን ስመ ንጉሥ ጽፈው ሥዕለ አንበሳ ቀርጸው ባንድ ወገን ስመ እግዚአብሔር ጽፈው ሥዕለ ኪሩብ ቀርጸው ይዘው መጡ ፤ ዘቄሣር ያለን እንደሆነ ዘእግዚአብሔር ይላልሳ፥ ዘእግዚአብሔር ያለን እንደሆነ ዘቄሣር ይላልሳ ብለን ምላሽ እናሳጣዋለን ብለው ነው ። እሱም በመጡበት ይጨነቁበት ብሎ የግራ የቀኙን አንድ ጊዜ ተናገረው ፤ እንዳይለዩት የማይለይ ነው ከእሳትም ቢያገቡት ሁሉም ይጠፋል ። አንድም አርአያ ቄሣር ሰውነታችሁን ለቄሣር አስገዙ አርአያ እግዚአብሔር ሰውነታችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ አንድም አፍአዊ ሰውነታችሁን ለቄሣር አስገዙ ውሳጣዊ ሰውነታችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ.
፳፪ ወሰሚዖሙ አንከሩ ወኃደግዎ ወኃለፉ።

፳፪ ምላሹን ሰምተው አድንቀው ትተውት ሄዱ ።

በእንተ ሰዱቃውያን ወትንሣኤ ምውታን።

፳፫ ወበይእቲ ዕለት መጽኡ ኀቤሁ ሰዱቃውያን እለ ይብሉ አልቦ ትንሣኤ ሙታን ግብ ፳፫ ፡ ፰ ።

፳፫ በዚያች ቀን ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን መጡ ።

፳፬ ወተስእልዎ እንዘ ይብሉ ።
ዘዳግም ፡ ፳፭ ፡ ፭ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፲፱ ፡ ሉቃስ ፡ ፳፡፳፰

፳፬ እንዲህ ብለው ጠየቁት ።
ኦ ሊቅ ሙሴ ጸሐፈ ለነ ለእመ ሞተ እኁሁ እንዘ አልቦ ውሉድ ያውስብ ብእሲተ እኁሁ ወያቅም ዘርዓ ለእኁሁ ።
መምር ሆይ ወንድሙ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ታናሽ ወንድሙ አግብቶ ስሙን የሚያስጠራ ልጅ ይውለድለት ብሎ ሙሴ ጽፎልናል ።
፳፭ ወሀለዉ ኀቤነ ፯ቱ አኃው ።
፳፭ ሰባት ወንድማማች ከኛ ዘንድ ነበሩ ።
ወዘይልሕቅ አውሰበ ወሞተ እንዘ አልቦ ውሉድ ።
ታላቁ ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ ።
ወኃደገ ብእሲቶ ለእኁሁ ። ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት ። ሐተታ ፤ የምትገባው ስለ ሆነ እንዲህ አለ ።
፳፮ ወከማሁ ካዕበ ካልዑኒ ወሣልሱኒ እስከ ፯ቲሆሙ አውሰብዋ ።
፳፮ እንደዚህም ሁሉ አንዱ እየሞተ አንዱ እየተተካ ሰባቱ ሁሉ አገቧት ።
ወኢኃደጉ ውሉደ ።
ሁሉም ልጅ ሳይወልዱ ሞቱ ።

፳፯ ወድኅረ ኵሎሙ ሞተት ይእቲ ብእሲት፣
፳፯ ከእሳቸው በኋላ እሱዋም ሞተች ።
፳፰ ወእመ ይትነሥኡ እንከ ምውታን ለመኑ እም፯ቲሆሙ ትከውን ብእሲተ ፣

፳፰ ሙታን በሚነሡበት ጊዜ ከሰባቱ ለማን ትሆናለች ።
እስመ ኵሎሙ አውሰብዋ መላው አግብተዋታልና

ሐተታ ፣ ሰዱቃውያን ትንሣኤ ሙታን የለም ይላሉ ፣ ፈሪሳውያን ግን ትንሣኤ ሙታን አለ እንደ ገና ከሚስቶቻችን ከልጆቻችን ጋራ እንኖራለን ይላሉ ፣ ትንሣኤ ሙታን ካለ ለማናቸው ትገባለች ይሏቸዋል ለመላው ያሏቸው እንደሆነ ዓለመ ዘሙት ናት ይሏቸዋል ላንዱ ያሏቸው እንደሆነ ዓለመ ግፍዕ ናት በወዲሁ ሥራት ይሠራባቸው በወዲያው ይከለከልባቸው እያሉ ምላሽ ያሳጧቸዋል እንደነዚያ መስሏቸው ጌታን ይጠይቁታል እሱም ይመልስላቸዋል ። እንድም ብእሲት ይህቺ ዓለም ሰባት እስከምጽአት የሚነሡት ነገሥታት ናቸው ፣ በፍጹም ተናገራቸው ። እስመ ኍልቍ ሰብእ በኀበ እብራያውን ፍጹም ውእቱ እንዲል ።

፳፱ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ
፳፱ ጌታ መለሰ ።
ወይቤሎሙ ስሕትክሙ በኢያእምሮ መጻሕፍት ።
የሥነ ፍጥረትን ነገር የሚናገር መጽሐፍን ባለማወቅ
ወኢኃይለ እግዚአብሔር ።
እምጻኤ ዓለማትነቱን ባለማወቅ በደላችሁ ።

ሐተታ፣ እያሥነማም ይሉታል እንጂ አልፈጠረም ይሉታል ቢሉ ጥንቱን አካል ያለውን አካል ሰጥቶ እያስነሣም ካሉት ይህን ዓለም እምኀበ አልቦ አምጥቶ አልፈጠረም ያሰኙባቸዋልና ፤ እንድም ስሕትክሙ ብለህ መልስ የትንሣኤ ሙታንን ነገር የሚናገሩ መጻሕፍትን ባለማወቅ ፣ ወኢኃይለ እግዚአብሔር የጌታችንን ትንሣኤ ባለማወቅ በደላችሁ ሐተታ ፣ ሙታን አይነሡም ብለዋል እንጂ ጌታን አልተነሣም ብለዋልን ቢሉ ሙታን አይነሡም ካሉ ጌታ አልተነሣም ማለት ነውና ።

፴ እመሰ የሐይው ምውታን ኢያወስቡ ወኢይትዋሰቡ ።

፴ ሙታን በሚነሡበት ጊዜ አያገቡም አይጋቡም ። አላ ከመ መላእክተ እግዚአብሔር ይከውኑ እሙንቱ በሰማያት እንደ መላእክት አንድ ወገን ሆነው በመንግሥተ ሰማይ ይኖራሉ እንጂ ፣

፴፩ ወበእንተ ትንሣኤ ሙታንሰ ኢያንበብክሙ ዘተብህለ ለክሙ እምኀበ እግዚአብሔር ዘይቤ

፴፩ አነ እግዚአብሔር አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ ።

፴፪ ትንሣኤ ሙታንማ እንዳለ ለማጠየቅ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ እኔ ነኝ ብሎ

፴፪ እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረውን አልተመለከታችሁምን አላወቃችሁምን ፣ ወእግዚአብሔርሰ ኢኮነ አምላከ ምውታን አላ አምላከ ሕያዋን እግዚአብሔር ግን የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ ነበሩኝ ሞቱብኝ ለማለት የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነኝ አላለም ። በነፍስ ሕያዋን ናቸውና ። ይቀድሱታልና እንዲያስነሣቸው ያውቃልና እንዲህ አለ ። ሐተታ ይህች ዓለም ዛሬ በስባቱ ዕለታት ትመገባለች ኋላ እንደምን ናት ቢሉት ኋላስ መዓልትና ሌሊት ክረምትና በጋ ብርሃንና ጨለማ የለም እንደ መላእክት አንድ ወገን ሁነው ይኖራሉ ብሏቸዋል ። ዛሬ ሥጋና ነፍስ ይሳሳባሉ ኋላ እንደምን ይሆናሉ አሉት ኋላስ መሳሳብ የለም ዓለሙም ዓለመ ነፍስ ነው ሥጋም ነፍስን መስላ እንደ መላእክት ሁነው ይኖራሉ አላቸው ። ዛሬ ሥጋዊውን ከንጉሥ እስከኳደሬ እስከ አቅራሪ መንፈሳዊውን ከሊቀ ጳጳስ እስከ ዓፃዌ ኆኅት ባለው አድሮ ይመግባል ። ኋላ እንደምነው ቢሉት ። ኋላስ ገዢና ተገዢ የለም፤ወአስኩብዎ ለውእቱ ሰይፍ ውስተ መካኑ እንዲል ። ገዢው አንድ እሱ ነው ። እንደ መላእክት አንድ ወገን ሁነው ይኖራሉ አላቸው ።

፴፫ ወሰሚዖሙ ሕዝብ እንከሩ ምሕሮቶ ።
፴፫ ሕዝቡ ሰምተው ትምህርቱን አደነቁ ።

በእንተ ዓቢይ ትእዛዝ እግዚአብሔር

፴፬ ወሰሚዖሙ ፈሪሳውያን ከመ ፈጸሞሙ አፉሆሙ ለሰዱቃውያን ተጋብኡ ኀቤሁ ኵሎሙ ኅቡረ
፴፬ ሰዱቃውያንን ምላሽ እንዳሳጣቸው ፈሪሳውያን ሰምተው ደስ ብሏቸው ባንድነት ወደሱ ተሰበሰቡ ። ሐተታ ቢስ የቢስ ቀን ክፉ የከፉ ቀን ብለው።

፴፭ ወተስእሎ ፩ ጸሐፊ እምኔሆሙ ።
፴፭ ከሳቸው ወገን አንድ ጸሐፊ ማለት ዐዋቂ ነኝ የሚል ጠየቀው ። እንዘ ያሜክሮ ሲፈትነው

፴፮ ሊቅ ዓይኑ ትእዛዝ ዓባይ በውስተ ኦሪት
፴፮ መምህር ደገኛው ትእዛዝ ማናቸው ነው ። እንድም በኦሪት ማናቸው ትእዛዝ ይበልጣል አለው
፴፯ ወይቤሎ አፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ልብከ ፣

፴፯ እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡናህ ውደደው ያለው ነው ።
ወበኵሉ ነፍስከ ።
በፍጹም ሰውነትህ ።
ወበኵሉ ኃይልከ ።
በፍጹም ዕውቀትህ
ወበኵሉ ሕሊናከ ።
በፍጹም ሕሊናህ ።

፴፰ ዛቲ ትእዛዝ ዓባይ ወቀዳሚት

፴፰ ይኸችውም መጀመሪያይቱ ትእዛዝ ይህች ናት ። እንድም ቀዳሚሆሙ ለአሕዛብ አማሌቅ እን ዲል ፡ ፊጽሞ ያገኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት ።

፴፱ ወካልእታኒ እንተ ትመስላ አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ ።

፴፱ ሁለተኛይቱም አፍቅር በማለት ዋጋ በማሰጠት የምትመስላት ፍቅረ ቢጽ ናት ።

፵ በእሊ ክልኤ ትእዛዝ ተሰቅሉ ኦሪት ወነቢያት

፵ በነዚህ በሁለቱ በፍቅረ ቢጽና በፍቅረ እግዚአብሔር ኦሪት ነቢያት ተጠብቀው ይኖራሉ ። ሐተታ ፡ ሁለቱ እንደ ሁለቱ ፍንጅ በምንቱ እንደ ሰምንቱ ጠንግ ሁነው ።

በእንተ ሙሴሕ ወልደ ዳዊት ።

፵፩ ወእንዘ ጉቡአን ፈሪሳውያን ተስእሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ።

፵፩ ፈሪሳውያን ባንድነት ተሰብስበው ሳሉ ጌታ ጠየቃቸው

፵፪ እንዘ ይብል ምንተ ትብሉ በእንተ ክርስቶስ

፵፪ የክርስቶስን ነገር ምን ትናገራላችሁ ብሎ

ወልደ መኑ ውእቱ ።

የማን ልጅ ነው ።

፵፪ ወይቤልዎ ወልደ ዳዊት ።

፵፪ የዳዊት ልጅ ነው አሉት ።

፵፫ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እፎ እንከ ለሊሁ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ይቤ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ ።

፵፫ ልጅማ ከሆነ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ እግዚእየ አብ እግዚእየ ወልድን በቀኜ ተቀመጥ ብሎ ነገ ሩ እለው እንዴምን ቻለ ። እስከ አገብኦሙ ለጸላ ኢትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ ። ጠላቶችህን በእጅህ ጭብጥ በእግርህ እርግጥ አድ ርጌ እስካስገዛልህ ድረስ ጸላዕት አይሁድ አጋንንት መናፍቃን ናቸው ። መከየደ እግር ያለው ሕዋርያት ሥልጣኑ መለኮት መሆኑ ገድሎች ነው ።

፵፭ ዘለሊሁ ዳዊት እግዚእየ ይቤሎ እፎ እንከ ይከውኖ ወልዶ ።

፵፭ ዳዊት ጌታዬ ያለው እንደምን ልጁ ይሆ ነዋል ። ይህንንም ሊቁ በዝማሬ እኪህዘ ልደተ ሥጋሁ ዘእምዘርዓ ዳዊት ብሎታል ። የአምላክነቱን ነገር ሲናገር ነው እንጂ በሥጋ ከዳዊት መወለዱን አሉ ብሎት አይደለም ብሏል ።

፵፮ ወአልቦ ዘክህለ አውሥኦቶ ቃለ ወአልቦ ዘተሀበለ ተሰእሎቶ ምንተኒ እምይእቲ ዕለት ።

፵፮ ከዚያች ቀን ጀምሮ ከዚያች ቀን ወዲህ ማንም ማን ሊጠይቀው ሊመልስለት የወደደ የደ ፈረ የለም ።

በእንተ መያልዋን ፈሪሳውያን ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

፩ ወእምዝ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለሕ ዝብ ወለአርዳኢሁ ።

፩ ከዚህ በኋላ ጌታ ለሕዝቡ ነገራቸው ።

፪ እንዘ ይብል ዲበ መንበረ ሙሴ ነበሩ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ። እብራ ፰ ፡ ፬ ።

፪ ጸሐፍት ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ማለት በሙሴ መምህርነት አሉላችሁ ።

፫ ኵሉ ዘይቤሉክሙ ግበሩ ።

፫ ያዘዟችሁን ፡ ሁሉ ሥሩ ።

ወዘመሐሩክሙ ዕቀቡ ።

ያስተማሯችሁንም ጠብቁ ።

ወዘከመ ምግባሮሙሰ ኢትግበሩ ።

እንደ ሥራቸው ግን አትሥሩ

እስመ እሙንቱ ይሜህሩ ለባዕድ ።

ለሌላ ያስተምራሉና ግበሩ ዕቀቡ ።

ወኢይገብሩ ።

እሳቸው አይሠሩትምና ኢትግበሩ ፡ እንድም ንግሩ እንጂ ግበሩ የለምም ኢትግበሩ በል

፬ ወየአስሩ ጾረ ዓቢየ ወክቡደ ወያሰክምዎ ለሰብእ ዲበ መትከፍቱ ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፵፮ ፡ ግብ ፲፭ ፡ ፲

፬ ጽኑ ሸክም አስረው ሰውን ተሸከም ይሉታል ወለሊሆሙሰ ኢይለክፍዎ በአጻብዒሆሙ ጥቀ ። እሳቸው ግን ስንኳ ሊሸከሙት በጣታቸው አይዳ ስሱትም ። እንድም ወየአስሩ ፡ ጽኑ ሥርዓት ሠር ተው ሰውን ጠብቅ ይሉታል ። ወለሊሆሙሰ እሳ ቸው ግን ስንኳን ሊሠሩት እንሠራዋለን ብለው አያ ስቡም ።

፭ ወኵሎ ምግባሮሙ ዘይገብሩ ለዓይነ ሰብእ ይገብሩ ። ዘኁል ፡ ፲፭ ፡ ፴፰ ። ዘዳ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ። ማር ፲፪ ፡ ፴፰ ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፵፫ ፡ ፳ ።

፭ የሚሠሩት ሁሉ ለሰው ይምሰል ነው ።

ወይሰፍሑ ዘርበታቲሆሙ ።

እንደጎልጎታ ያለ አላቸው ያን ባደባባይ ዘርግተው ይታያሉ ወየዓብዩ አዝፋረ አልባሲሆሙ የልብሳቸ ውን ዘርፍ አስፍተው ያስጥሉታል ፤ ሐተታ ፡ ጌታ ሙሴን በልብሳችሁ ሰማያዊ ሐር አስጥሉ ብሎታል ለጊዜው ሰማይ የሚመስል ባሕር ከፍሎ አሻገር ኋችሁ ሲል ነው ፍጻሜው ግን ሰማያዊ ሕግን ጠብቁ ሲል ነው ፡ ከሕዝቡ ይልቅ እኛ እንጠብቃ ለን ለማለት እሳቸው እያሰፉ የሚያስጥሉ ሁነ ዋል ፡ እንድም አልፈው አልፈው ያስጥሉታል እንደ ሱሲ ጦጣብር እንደቀሸ መሬ መታጠቂያ እንደ መረቫት ፡ እንድም ፲ቱ ቃላትን በልብሳቸው ይጽፉ ነበር ከሰውነታችን የተረፈው በልብሳችን

አለ ለማለት ቄስ ዐፄ ምህርካ ድንግል ኢየሱስ ናዝራዊ ብለው በልብሳቸው ጽፈው እንደነበረ ፤

፮ ወያፈቅሩ ርእሰ ምርፋቃት በውስተ ምሳሐት
፮ በምሳም ጊዜ በላይ መቀመጥን ይወዳሉ ምንጣፍ መጨጊያ ካለበት ወጥ ከተደራረበበት እንጀራ ከበዛበት ጽዋ ከሚጀመርበት ይህ ለጊዜው ጥቅም ያለበት ነው ፤
ወንቢረ ፍጽም በውስተ አዕዋዳት ።
ባደባባይ ፊት ለፊት መቀመጥን ይወዳሉና

፯ ወተአምኖ በውስተ ምሥያጣት
፯ ባደባባይ እጅ ሊነሷቸው ሊያከብሯቸው ይወዳሉ ፤
ወይበልዎሙ ሰብአ መምህራን ፤
መምህራን ይሏቸው ዘንድ

፰ አንትሙሰኬ ኢትሰምዩ መምህረ በዲበ ምድር ፤ ያዕ ፤ ፫ ፤ ፩ ።

፰ እናንተስ ምድራዊ መምህር አይኑራችሁ ፤
እስመ ፩ዱ ውእቱ መምህርክሙ ፤
መምህራችሁ አንድ ሰማያዊ ክርስቶስ ነውና ፤ ሐተታ ፤ ዲበ መንበረ ሙሴ ነበሩ ያለውን ማፍረሱ ነው ቢሉ ያንም እንጂ ወዘከመ ምግባርሙሰ ኢትግበሩ ባለው አፍርሶታል እንድም ለጣዖት ስገዱ ሃይማኖታችሁን ካዱ የሚል መምር አይኑራችሁ ሲል ነው

፱ ወኢትረድኡ ለክሙ አበ በዲበ ምድር ።
ሚልክ ፩ ፤ ፮ ።

፱ ምድራዊ አባት አይኑራችሁ ፤ እስመ ውእቱ አቡክሙ ሰማያዊ ።
አባታችሁ አንዱ ሰማያዊ ክርስቶስ ነውና ፤ ሐተታ አክብር አባከ ወእመከ ይላል የለም ቢሉ ከአክብሮተ አብ ወአምአክብሮተ እግዚአብሔር እንዲበልጥ ለማጠየቅ ፤ እንድም ለጣዖት ስገዱ የሚል አባት አይኑራችሁ ሲል ነው ፤ ዘኢጋደለ አባሁ ወእሞ አይክል ይፀመደኒ እንዲል ፤
አንትሙሰ አኃው ዚአክሙ እናንተስ ወንድማማች ናችሁ ።

፲ ወኢትሰመዩ እግዚእ በዲበ ምድር ።
፲ ምድራዊ ጌታ አይኑራችሁ ፤ ሐተታ ዘቄሣር ሀቡ ለቄሣር ብሎ የለም ቢሉ ፤ ያንም እንጂ ወዘ እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ባለው አፍርሶታል እንድም ለጣዖት ስገዱ ሃይማኖታችሁን ካዱ የሚል ጌታ አይኑራችሁ ሲል ነው ፤
እስመ ፩ዱ ውእቱ እግዚእክሙ ክርስቶስ ፤
ሰማያዊ ጌታችሁ አንድ ክርስቶስ ነውና ።

፲፩ ወባሕቱ ዘይፈቅድ እምኔክሙ ይኩን ዓቢየ ይኩንክሙ ገብረ ።

፲፩ ከናንተ ወገን በላይ ሊሆን የወደደ አገልጋይ ይሁናችሁ ወዘይፈቅድ እምኔክሙ ይኩን ሊቀ ይኩንክሙ ላዕከ ።
ገዢ ሊሆን የወደደ ተገዢ ይሁናችሁ ።

፲፪ እስመ ዘአዕበየ ርእሶ የኃሥር ሉቃ፤ ፲፬፤ ፲፩
፲፪ ራሱን ያከበረ ይዋረዳልና ።
ወዘአትሐተ ርእሶ ይከብር
ራሱን ያዋረደ ይከብራልና ።

፲፫ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ።
፲፫ ጸሐፍት ፈሪሳውያን እናንተ ግብዞች ወዮላችሁ።
እለ ትበልዑ አብያተ መበለታት በምክንያተ እንዋ ጸሎትክሙ ። አብዝተን እንጸልያለን በማለት ምክንያት የድሆችን ገንዘብ የምትበሉባቸው ። ማዕዜሙ አገብር ቤተ ለርእሰየ ያጠርያ ቤተ እምጽድቀ ዘአሁን እንዲል ፤ አብዝተው ሲጸልዩ ያዩዋቸው እንደሆነ የባሎቻችንን ነፍስ ያስምሩልናል ልጆቻችንን ያሳድጉልናል እያሉ ይሰጧቸዋልና ።
ወበእንተ ዝንቱ ትረክቡ ኩነኔ ፈድፋደ ።
ስለዚህ ጽኑ ፍዳ ትቀበላላችሁ

፲፬ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን ።

፲፬ እናንት ግብዞች ወዮላችሁ
እስመ ተዓፅዉ መንግሥተ ሰማያት ቅድመ ገጹ ለሰብእ በሰው ፊት መንግሥተ ሰማይን ትዘጉበታላችሁና ፤ አብንት ሁናችሁ እንዳይገቡ ታደርጓቸዋላችሁ ማለት ነው ።
አንትሙኒ ኢትበውዑ ፤
እናንተም አትገቡ ።
ወለእለኒ ይበውዑ ትከልዕዎሙ በዊእ ።
የሚገቡትንም አብንት ሁናችሁ እንዳይገቡ ታደርጓቸዋላችሁ ።
፲፭ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን ።
እናንተ ግብዞች ወዮላችሁ ።
እስመ ተዓውዱ ባሕረ ወየብሰ ከመ ታግብኡ አሐደ ፈላሲ
፲፭ ትገዙሩ ሲል ነው ከጣዖት ከኃጢአት ፈልሶ የመጣውን ትገዙሩ ዘንድ የብሱን በእግር ባሕሩን በሐመር ትዞራላችሁና ወተጠሚቆ ትረሰይዎ ወልደ ገሃነም ።
የገሃነም ልጅ ማለት ከተገዘረም በኋላ ተማልታችሁት ገሃነም ትወርዳላችሁ ።
፲፮ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን እምሀርተ ዕውራን ።
፲፮ እምርሁት ይላል የዕውራን አእምር መሪዎች መምሮች ወዮላችሁ ።
እለ ትብሉ ዘመሀለ በቤተ መቅደስ ይጊጊ ።

በቤተ መቅደስ ቢምሉ ዕዳ አይሆንበትም የምትሉ። ወዘሰ መሐለ በወርቀ ቤተ መቅደስ ኢይጌጊ ። በመብዑ ቢምል ግን ዕዳ ይሆንበታል የምትሉ ።

፲፯ ዓብዳን ወዕውራን ።
፲፯ እናንት ዐላዋቆች ሰነፎች ።
ኅይ የዓቢ ።
ማን ይበልጣል ።
ወርቅኑ ፤ ወርቅ ይበልጣልን ወሚመ ቤተ መቅደስ ዘይቄድሶ ለወርቅ ።
ወይም ወርቁን የሚያከብረው ቤተ መቅደስ ይበልጣልን አኮኑ ቤተ መቅደስ ዘይቄድሶ ለወርቅ ። ወርቁን የሚያከብረው ቤተ መቅደስ ይበልጥ የለምን

፲፰ ወዘሰ መሐለ በምሥዋዕ ኢይጌጊ ።
፲፰ በምሥዋዑ ባለ በታቦቱ የማለ ዕዳ አይሆንበትም ትላላችሁ ወዘሰ መሐለ በጽንሐሕ ዘላዕሌሁ ይጌጊ ትብሉ ።
በመሥዋዕቱ የማለ ግን ዕዳ ይሆንበታል ትላላችሁ

፲፱ እ ዓብዳን ወዕውራን ።
፲፱ እናንት ዐላዋቆች ሰነፎች ።
መኑ የዓቢ ።
ማን ይበልጣል ።
ጽንሐሕኑ ወሚመ ምሥዋዕ ።
መሥዋዕቱ ይበልጣልን ወይስ ታቦቱ ይበልጣል ። አኮኑ ምሥዋዕ ዘይቄድሶ ለጽንሐሕ ።
መሥዋዕቱን የሚያከብረው ታቦቱ ይበልጥ የለምን ? ከታቦትና ከመሥዋዕት ማን ይበልጣል ቢሉ እስኪለወጥ ታቦት ይበልጣል ከተለወጠ በኋላ ግን አንድ ነው ከደሙ ደሙ አይበልጥም ከታቦትና ከመስቀል ማን ይበልጣል ቢሉ በሀገራቸው ሚሮን ይቀባሉና ሁሉም እኩል ነው ። በሀገራችን ግን ሚሮን አይቀባምና ታቦት ይበልጣል ፤ መስቀል ያንሳል ።

፳ ዘኪ መሐለ በምሥዋዕ መሐለ ቦቱ ።
፳ በታቦቱ የማለ በታቦቱ ማለ
ወበኵሉ ዘይነብር ዲቤሁ ።
በታቦቱ ላይ ባለው ሁሉ ማለ ።
፳፩ ወዘሂ መሐለ በቤተ መቅደስ መሐለ ቦቱ
፳፩ በቤተ መቅደስ የማለ በቤተ መቅደስ ማለ
ወመሐለ በኵሉ ዘይነብር ውስቴቱ ።
በቤተ መቅደስ ውስጥ ባለው ሁሉ ማለ ።
፳፪ ወዘሂ መሐለ በሰማይ መሐለ መንበሮ ለእግዚአብሔር ።
፳፪ በሰማይ የማለ በዙፋኑ ማለ ።
ወበዘይነብር ዲቤሁ ።
በሰማይም ባለው ማለ ።
እንድም ዘሂ መሐለ ብለህ መልስ በትስብእት የማለ በትስብእት ማለ ወበዘይነብር ዲቤሁ ተዋሕዶትም ባለው በመለኮት ማለ ። ወዘሂ መሐለ በሰማይ ፤ በመለኮት የማለ በመለኮት ማለ ወበዘይነብር ዲቤሁ ፤ ተዋሕዶትም ባለ በትስብእት ማለ ።

፳፫ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን እለ ታበውኡ ዐሥራተ ጼጐ ለእሕዛብ ሉቃ ፤ ፲፩ ፤ ፵፪ ።
፳፫ ያብሽ ፤

ወለሲላን ፤ የድንብላል ወለከሙን ።
ፌጦ ። እንድም የባሕር ከሙን ካሥር አንድ የምትሰጡ ። ወኀደግሙ ዘየዓቢ ትእዛዛተ ኦሪት ።
በኦሪት የታዘዘውን ደገኛውን ትእዛዝ የምታስቀሩ ፍትሐ ። ፍርድን ማለት ዘቄጣር ሀቡ ለቄጣር ያለውን ወጽድቀ ። ምጽዋት አበደሮ እመ ሥዋዕት ያለውን ፤ ወሃይማኖተ ። ወዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ያለውን የምታስቀሩ ።
ዘኒ መፍትው ትግበሩ ።
ይህንስ ልታደርጉ ይገባል ማለት ዲጋትን ልትሰጡ ይገባል ወዝክተኒ ኢትኅድጉ ።
ያንንም አትተው ማለት ጥቃቅኑንም አታስቀሩ ።

፳፬ አምርሀተ ዕውራን እለ ጸጹተ ትነጥፉ ።
፳፬ ጥቃቅኑን ካሥር አንድ አጥርታችሁ የምትሰጡ ። ወይነጥፎሙ ለደቂቀ ሌዊ እንዲሉ ወገመለሰ ትውኅጡ ።
ታላላቁን ስውራችሁ የምታስቀሩ መሪዎቻችሁ ፤

፳፭ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን እለ ተሐፅቡዎ ለጽዋዕ ወለጻሕል እንተ አፍአሁ ።
፳፭ የሕል ጽዋውን ውጭውን የምታጥቡት ግብዞች ወዮላችሁ ወእንተ ውስጡሰ ምሉእ ሐይደ ወትዕግልት ፤
በውስጥ ግን ቅሚያን የተመላ ነው ፤ በአሰበ ደነስ በመማለጃ ሰርቀው ቀምተው ያመጡታልና ፤ እንድም በዚህ የመጣውን ይበሉበታልና ።
፳፮ ኦ ፈሪሳዊ ዕዉር ቅድመ ሕጽቦ ለጽዋዕ ወለጻሕል እንተ ውስጡ
፳፮ አንት ዐላዋቂ ፈሪሳዊ ጻሕል ጽዋውን አስቀድመህ ውስጡን እጠበው ።
ከመ ይኩን ንጹሐ እንተ አፍአሁኒ ።
በአፍኣም ንጹሕ ይሆን ዘንድ እንድም እለ ጸጹተ ትነጥፉ ብለህ መልስ ጥቃቅኑን ኃጢአት አጥርታችሁ የምትናገሩ ። ወገመለሰ ። ታላላቁን ስውራችሁ የምታስቀሩ ። እለ ተሐፅቡዎ ጻህለ ጽዋ ሰውነታችሁን በአፍኣ ንጹሕ የምታደርጉ ። ወእንተ ውስጡሰ ። በውስጥ ግን ኃጢአትን የተመላ ነው ቅድመ ሕፅቦ ፤ አስቀድመህ ፃሕል ጽዋ ሰውነትህን በውስጥ ንጹሕ አድርገው ። ከመ ይኩን በአፍኣም ንጹሕ ይሆን ዘንድ የሥጋ ንጽሕ ስንፍስ አይሆንም ነፍስ የነፃች እንደሆነ ግን ለሥጋም ይተርፈዋል ቅዱሳን የበቁ እንደሆኑ የነፍሳቸው ለሥ

ጋቸው ፣ የሥጋቸው ለልብሳቸው ተርፎት በልብሳቸው በመቋሚያቸው በጭራቸው ከመፈወስ ይደርሳሉና ።

፳፯ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን እስ ትመስሉ መቃብረ ግብሱሳን እለ እም አፍአሆሙ ያስተርእዩ ሠናያን

፳፯ በአፍአ አጊጠው የሚታዩ የተለሰኑ መቃብራትን የምትመስሉ ግብዞች ወዮላችሁ ።
ወእንተ ውስጦሙሰ ምሉአን አዕፅምተ ወዘርኩስ ።
ርኩስ ነገር ማለት በውስጥ ግን አዝት ፈሶ ኸርማቱ ተፀማጥሶ አጥንቱ ተከስክሶ ሥጋው ተልከስክሶ ለዓይን የሚያስከፋ ላፍንጫ የሚከረፋ ነገር ያለባቸውን መቃብራት የምትመስሉ ።

፳፰ ከማሁ አንትሙኒ ትጸድቁ ለዓይነ ሰብእ

፳፰ እንዲያ በአፍአ አጊጠው እንዲታዩ እናንተም በአፍአ ደጋግ መስላችሁ ትታያላችሁ ።
ወእንተ ውስጥከሙሰ ምሉአን አንትሙ ዓመፃ ወአድልዎ በውስጥ ግን ኃጢአትን የተመላችሁ ናችሁ ።

፳፱ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን እስ ተሐንጹ መቃብሪሆሙ ለነቢያት ወትሤንዩ ዝጎርሙ ለጻድቃን ።

፳፱ ደጋግማ ካልሆኑ የነቢያትን መቃብር ያንጻሉ ይበሉን ብላችሁ የነቢያትን መቃብር የምታንጹ የጻድቃንን መቃብር የምታስጌጡ ግብዞች ወዮላችሁ
፴ ወትብሉ ሶበ ሀሎነ በመዋዕለ አበዊነ እም ኢተሳተፍነ ምስሌሆሙ በከዒወ ደመ ነቢያት ።
፴ ባባቶቻችን ዘመን ኑረንስ ቢሆን የነቢያትን ደም በማፍሰስ ከባቸው ጋራ አንድ ባልሆንም ነበር ትላላችሁ ።
፴፩ ናሁኬ ለሊክሙ ትከውኑ ስምዓ ከመ ደቂቆሙ አንትሙ ለቀተልተ ነቢያት ።
፴፩ ነቢያትን ለገደሉ ሰዎች ልጆቻቸው እንደሆናችሁ እነሆ ትመሰክራላችሁ ።
፴፪ አንትሙሂ ፈጽሙ መሥፈርተ አበዊክሙ
፴፪ እናንተም ካባቶቻችሁ የቀረውን ፈጽሙ አጸንሆ ለአሞሬዎን እስከ አመ ይትፌጸም ኃጢአቱ እንዲል ፣ እሱስ አይዛቸውም እንዳይተውት ያውቃልና እንዲህ አለ እንጂ ። የጌታ ሞት ለነቢያት ሞት ምልአት እንደሆነ የውሉድም ኃጢአት ለአበው ኃጢአት መልአት ይሆናል ።
፴፫ አ ትውልደ አራዊተ ምድር አፎ ትክሉ አምስጦ እምኰነኔ ገሃነም ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፯ ።
፴፫ እናንት የምድር አባብ ልጆች በገሃነም ከሚመጣው ፍዳ መዳን እንደምን ይቻላችኋል ።
፴፬ ወበእንተዝ እነ እፌኑ ኀቤክሙ

፴፬ ሶበሰ ሀሎነ የምትሉ ስለሆነ ስለዚህ ነገር ወደናንተ እልካለሁ ነቢያት ፣

ነቢያት ፣ ፫	አርድዕትን
ወሐዋርያተ	ሐዋርያትን
ወጠቢባተ ።	ሹማምንትን
ወጸሐፍተ	መምህራንን

መተርጕማንን እልካለሁ ።
ቦ እምኔሆሙ ዘትቀትሉ ፣ ከባቸው ወገን የምትገድሉት አለ
ወቦ እምኔሆሙ ዘትሰቅሉ ።
የምትሰቅሉት አለ ።
ወቦ እምኔሆሙ ዘትቀሥፉ በምኩራባቲክሙ ።
በምኩራባችሁ አግብታችሁ የምትገርፉት አለ ።
ወትሰድድዎሙ እምሀገር ውስተ ሀገር ።
ካንዱ አገር ወዳንዱ አገር አስወጥታችሁ የምትሰዱት አለ ።

፴፭ ከመ ይብጻሕ ላዕሌክሙ ደመ ኵሉሙ ጻድቃን እምደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ ዘቀተልክምዎ በማእከለ ቤተ መቅደስ ወምሥዋዕ ። ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፰ ፡ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ፡ ሕጹጸ ፳፬ ፡ ፳፪ ።

፴፭ ከአቤል ደም ጀምሮ በዕቃ ቤትና በቤተ መቅደስ መካከል በገደላችሁት እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በዓለም የፈሰሰ የጻድቃን ደም ፍዳ ሊደረግባችሁ ንድ ፣ ሐተታ ፣ ጠርዙንና ጠርዙን ይዞ ተናገረ ። ለበማዕታተ ብሊት ጥንታቸው አቤል ፍጻሜያቸው ዘካርያስ ነውና ፣ አንድም ግፍ ለግፍ ሲያነጻጽር አቤል የሞተ በግፍ ነው ዘካርያስም የሞተ በግፍ ነውና ። አንድም ደመ ሰከየትንና ደመ ሰከየትን ሲያነጻጽር መልአኩ ለሄኖክ ማኅደረ ኃጥአንን አያዞረ ሲያሳየው አንዲት ነፍስ እየተንጸረጸረች ስታካስስ ስታሳጣ አይቶ ዘመንፈስ ዘመኑ ብሎ ጠየቀው ዘአቤል ዘቀተሎ እኁሁ ። ይብኪ ኪያሁ እስከ አመ ይትኃጎሉ ደቂቁ እምገጸ ምድር በማየ አይኅ ብሎ ታል ። የዘካርያስም ደም ፫ ዘመን ሲፈላ ኑሯል ። ጥጦስ አይቶ ምንድነው ብሎ ጠየቀ ። ደግ ሰው ነበረ በግፍ አስገድለውት ነው አሉት ከኛዎቹ ወገን ሰባት ሰዎች አስመጥቶ ቢያሳርድ መፍላቱን ትቷል ። ከዕቃቤትና ከቤተ መቅደስ መካከል ያስገደላችሁት አለ ፣ የምትሻው ሕፃን ከዘካርያስ ቤት አለ ሲፀንስ ያባቱን እንደበቅ የዘጋ ሲወልድ የፈታ ብለው ነገሩት ። አስጠርቶ እንዲህ ያለ ብላቴና አለ ብሎ ጠየቀው ። አዎን ምነው ጠየቅኸኝ አለው ይህን ልትነግረኝ ነው ሂድ አለው ። ይህ ዓላዊ አለ ነገር አል ጠየቀኝም ልጄን ሊያስገድለው ነው ሁሉት ሳላ ድርበት ብሎ ከቤተ መቅደስ አግብቶ ሲጸልይለት ግደሉ ብሎ ጭፍራ ላከ ። ከቤት ቢሄዱ አጡት ኋላ መልአኩ ለኤልሳቤጥ ይህ ዓላዊ ልጅሽን ሊያስ

ገድልብሽ ነው ገዳም ይዘሽ ሂጂ አላት ገዳም ይዛ ሂዳለች ከቤተ መቅደስ ቢሄዱ እሱን አገኙት ከዚያ ገድለውታል ። አንድም የምትሻት ቤት ከልጅዋ ጋራ ከዘካርያስ ቤት ትገባለች ትወጣለች ብለው ነገሩት አስጠርቶ ወስዶ እኔ የምሻት ቤት ካንተ ቤት አስችን አለው እዎን አለው ። ምነው ያልነገርከኝ አለው እመቤቴን የሷን ሞት ለኔ ያድርገው አለው ። እንዳየህ ውጋው አለው ወጉት ደም ተኩሶት ሂዶ ከቤተ መቅደስና ከዕቃቤት መካከል ወድቋል ።

፴፮ እማን እብለክሙ ከመ ዝንቱ ኵሉ ይበጽሐ ለዛቲ ትውልድ ።

፴፮ በቤተ አይሁድ ይህ ሁሉ እንዲደረግባት በውነት እነግራችኋለሁ ።

ዘከመ ኄሳ ለኢየሩሳሌም ።

፴፯ ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም እንተ ትቀትሎሙ ለነቢያት ወትዌግሮሙ ለሐዋርያት እለ ተፈነው ኀቤሃ ። ሉቃ. ፲፫ ፡ ፴፬ ።

፴፯ በመምህርነት ወዳንች የተላኩ ነቢያትን ያጠፋሻቸው ሐዋርያትን የተጣላሻቸው ቤተ አይሁድ ሚመጠነ ፈቀድኩ አስተጋብኦሙ ለውሉድኪ ከመ እንተ ታስተጋብእ ዶርሆ ዕጕሊሃ ታኅተ ክነፊሃ ። ዶሮ ልጆቿን በክንፏ እንድትሰበስብ ማለት ነቢያት ሕዝቡን አንድ ያደርጓቸው እንደ ነበረ ልጆችሽን በትምህርት አንድ አደርጋቸው ዘንድ ምን ያህል ወደድኩ ።

ሐተታ ፡ ዶርሆ አላቸው ነቢያትን ፡ ዶሮ ወተት የላትም ልጆቹዋን የምታሳድግ ስው በጸረበት ነው ነቢያትም በጻዕር የተገኘውን ነውና ቢያስተምሩ የነበረ መልአክ የነገራቸውን መንፈስ ቅዱስ የገለጣላቸውን ። ወአበይክሙ አናምን አላችሁ ።

፴፰ ናሁ ይትኀደግ ለክሙ ቤትክሙ በድወ ።

፴፰ እነሆ ቤተ መቅደስ ትፈርሳለች ።

፴፱ እማን እብለክሙ ኢትሬእዩኒ እምይእዜ እስከ ሶበ ትብሉ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ።

፴፱ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም ብየ በእውነት እነግራችኋለሁ ። ሆሣዕና አላለፈም ቢሉ የተመቸ ፡ አልፏል ቢሉ ምጽአትን ያያል ።

በእንተ ዘአቅደመ ነጊረ ሙስናሃ ለቤተ መቅደስ

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

፩ ወወፂአ እግዚእ ኢየሱስ እምቤተ መቅደስ ሖረ ።

፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሄደ ።
ወቀርቡ አርዳኢሁ ወአርአይዎ ንድቀ ሕንጻሁ ለቤተ መቅደስ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው የቤተ መቅደስን ሥራ አሳዩት ማለት እንዲህ ቢያምር ይፈርሳል ትላለህ አሉት ፡ የጧት ፀሐይ ወድቆበት ሲያሸበርቅ አይተው

፪ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ መለሰ ፤

፪ ወይቤሎሙ ትሬእዩኑ ዘንተ ኵሎ ፤
ይህን ሁሉ ታያላችሁን ማለት ይህን ይደንቃችኋልን እማን እብለክሙ ኢይትኀደግ ዝየ እብን ዲበ እብን ዘኢይትነሠት ።
የማይፈርስ ሁኖ ደንጊያ በደንጊያ ላይ አይቀርም ብየ እንዳይቀር በውነት እነግራችኋለሁ ሐተታ ፡ ከጥጦስ ሠራዊት አንዱ ደንጊያ ቢፈነቅል ድስት ሙሉ ወርቅ አገኘ እንደዚያ እናገኛለን እያሉ ቤተ መቅደስን ሲያፈርሷት ፩ ፡ ፩ ደንጊያ አልደረሳቸውም አንድም ትሬእዩኑ ብለህ መልስ ይህን ይደንቃችኋልን ይህስ የሰው ሕንጻ ነው እማን እብለክሙ ሕንጻ እግዚአብሔር ሰው ይፈርሳል ይበሰብሳል ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፫ ወእንዘ ይነብር እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት ቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ ።

፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ወደሱ ቀረቡ ወይቤልዎ እንተ ባሕቲቶሙ ለብቻቸው ጠየቁት ሦስቱ ባለሟሎቹ እንድርያስን ጨምረው ይጠይቁታል ። ንግረነ ማእዜ ይከውን ዝንቱ ወናሁ ይትኀደግ ለክሙ ቤትክሙ በድወ ብሎ ነበርና ቤተ መቅደስ የሚፈርስበት ምን ጊዜ ይሆናል ።
ወምንትኑ ተአምሪሁ ለምጽአትከ ።
እማን እብለክሙ ኢትሬእዩኒ ብሎ ነበርና የምጻትህስ ወለኅልፈተ ዓለም ።
የኅልፈተ ዓለምስ ምልክቱ ምንድነው አሉት ።

፬ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ዑቁ ኢያስሕትክሙ ኢሎ ፡ ፭ ፡ ፮ ።

፬ እንዳያስቷችሁ አስተውሉ አላቸው ።

፭ እስመ ብዙኃን ይመጽኡ በስምየ እንዘ ይብሉ አነ ውእቱ ክርስቶስ ።

፭ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ ብዙ ሰዎች በኔ ስም ይነሣሉና ፡ ታሪክ ባማራ መንግሥት ጊዜ ዘክርስቶስ ይሉኛል ብሎ ተነሥቶ እንደነበረ ሰቅለው ገድለውታል ከሱ ጋራ ፯ መቶ ሰዎች ሙተዋል ሰማዕታተ ዘክርስቶስ ተብለዋል ።
ወያስሕትዎሙ ለብዙኃን ፡ ብዙ ሰዎችን ያስታሉ ።

፮ ወሶበ ሰማዕክሙ ።
ጾር ሲሰበሰብ ፤

፯ ወአጽባዕተ ።
ጋሻ ለጋሻ ሲላጐድ ፤
ወድምፀ ጸባኢት ፤
ገድሎ ሰልቦ ሲያገር ብትሰሙ
ዑቁ ኢትደንግፁ ።
እንዳትደነግጡ አስተውሉ ፤

እስመ ግብተ ሀለዎ ይኩን ዝንቱ ኵሉ ።
ይህ ሁሉ ፈጥኖ ይደረግ ዘንድ አለውና ።
ወባሕቱ አኮ በጊዜሃ ዘየኃልቅ፤ነገር ግን ያን ጊዜ የሚፈጸም አይደለም ።

፯ ወይትነሥኡ ሕዝብ ዲበ ሕዝብ ።
፯ ሕዝበ ሮም በሕዝበ እሥራኤል ላይ በጸላትነት ይነሡባቸዋል ። እንድም ወይትነሥኡ ሕዝብ ብለህ መልስ ሕዝበ እሥራኤል በሕዝበ እሥራኤል ላይ ፤ ነገሥተ እሥራኤል በነገሥተ እሥራኤል ላይ በጸላትነት ይነሡባቸዋል ።

ሐተታ ፤ ቀን ከጥጦስ ሠራዊት ጋራ ሲዋጉ ይውላሉ ። ማታ ከኔ ወገን አነግሥ ከኔ ወገን አነግሥ እያሉ ስንዝር ስንዝር ሙሉ ሾተል አልፎ ሲሄድ አበጅተው አንዱ ባንዱ እየሸጐጠበት ይሄዳል ገዳዩ ስላልታወቀ ሞተ ዕውር ተብሏል፤እንድም ሕዝበ ሮም በሕዝበ እሥራኤል ላይ በጸላትነት ይነሡባቸዋል ሕዝበ ሮም ያላቸው ቅሉ ከአርጳሚስ ጋራ የሄዱ የአርጳሚስ ወገን ናቸው ።
ወነገሥት ላዕለ ነገሥት ።
ነገሥተ ሮም በነገሥተ እሥራኤል ላይ በጸላትነት ይነሣሉ ። ነገሥተ ሮም ያላቸው ቅሉ የአርጳሚስ ልጆች ናቸው ።
ወይመጽእ ረኃብ ወብድብድ ፤
ወድልቅልቅ ውስተ ኵሉ በሐውርት ።
በየሀገሩ ረኃብ ቸነፈር ሽብር ይደረጋል ።
፰ ወዝንቱ ኵሉ ቀዳሚሁ ለሕማም ውእቱ።
፰ ይህ ሁሉ የመከራው መጀመሪያ ነው ማለት በጥጦስ ለሚደረገው መከራ ፊት አውራሪ ነው ። ቀዳሚሁ የጥጦስ ሕማም የሐሳዊ መሲሕ ቀዳሚሁ የሐሳዊ መሲሕ ፤ ሕማም የምጽአት ።
፱ አሜሃ ይትባጽሑክሙ ወይሚጥውክሙ ለምንዳቤ ። ማቴ.፲ ፤ ፲ ፤ ፯ ። ሉቃ ፤ ፳፩ ፤ ፲፪ ። ዮሐ ፤ ፲፭ ፤ ፳ ፤ ፲፯ ፤ ፪ ።
፱ ያን ጊዜ ስጸዋትወ መከራ አሳልፈው ይሰጧችኋል ።
ወይቀሥፉክሙ ።
ከምኵራባቸው አግብተው ይገርፏችኋል ። ወይቀትሉክሙ ይጸዷችኋል ።
ወትከውኑ ጽሉዓነ በኀበ ኵሉ ሰብእ በእንተ ስምየ። ሰለስሜ ማለት በኔ ስም ስላመናችሁ በኔ ስም ስላስተማራችሁ በኔ ስም ስለተጸራችሁ ሁሉ ይጸላችኋል
፲ ወይእተ አሚረ የዓልዉ ብዙኃን ሃይማኖቶሙ ።
፲ በዚያን ጊዜ ብዙ ሰዎች ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ ።
ወይጸልዑ በበይናቲሆሙ ።
እርስበርሳቸው ይጣላሉ ።
ወያገብኡ ቢጾሙ ለሞት ይትቃተሉ ።
አንዱ አንዱን ይጸላዋል ።

፲፩ ወብዙኃን ሐሳውያን ነቢያት ይመጽኡ ።
፲፩ በመምህራን የሚያብሉ መምህራንን የሚያሳብሉ ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉ ።
ወያስሕትዎሙ ለብዙኃን ።
ብዙ ሰዎችን ያስቷቸዋል ።

፲፪ ወእምብዝኃ ዓመፃ ወእከይ ተሐጽጽ ፍቅር እምብዙኃን ።

፲፪ ከሐሰትና ከኃጢአት ብዛት የተነሣ ፍቅር ከብዙ ሰዎች ታንሳለች። ትቈኵስ ፍቅር ይላል አብነት የሐጽጽ ሲል ነው ። ወይቈኵሱ ከመ ይቅብዑ መልአከ ወንጌሥ እንዲል ። የእክስን ባነገሡ ጊዜ በእልፍ በእልፍ ይቈጠሩ የነበሩ እሥራኤል ዐሥር ሠረገላ አምሳ ፈረሰኛ ሺህ እግረኛ ሁነው ተገኝተዋል ።
ወብዙኃን የዓልዉ ሃይማኖቶሙ ወፍቅሮሙ ።
ብዙ ሰዎች ሃይማኖታቸውን ምግባራቸውን ይለውጣሉ ።

፲፫ ወዘሰ አዘለፈ ትዕግሥቶ ውእቱ ይድኅን።
፲፫ ፈጽሞ መከራውን የታገሠ ከፍዳ የሚድን እሱ ነው ። እስከ ፍጻሜ ይላል አብነት እስከ ዕለተ ሞቱ ታግሦ መከራ የተቀበለ ከፍዳ የሚድን እሱ ነው ።

፲፬ ወይሰበክ ዝ ወንጌለ መንግሥት ውስተ ኵሉ ዓለም ።

፲፬ የመንግሥት ወንጌል ማለት ጌትነቱን የምትናገር ወንጌል ባ፷ቱ ማዕዘን ትነገራለች በእስላም ቤት ስንኳ ሳይቀር ትገኛለች ። ታሪክ በሀገራችን ቴዎድሮስ በሀገራቸው ዮሐንስ የሚባል ይነግሣል የኛም ሄዶ ያም መጥቶ በእስክንድርያ ሦስት ቀን ይዋጋሉ አራቱ ሊቃነ ጳጳሳት የክርስቲያን ደም ለምን ይፈሳል መሥዋዕት ሠውተን በመሥዋዕቱ ምልክት በታየለት ሃይማኖት ይጽና ይሏቸዋል ሁሉም በያሉበት መሥዋዕት ያቀርባሉ ። የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት በሠዋው እን ውእቱ ክርስቶስ ብሎ በርግብ አምሳል ወርዶ ይመሰክራል ከዚህ በኋላ በሃይማኖት አንድ ይሆናሉ በግቢ ይገናኛሉ እንደዚህ የሚል ከምን አለ ቢሉ ከገድለ ፊቅጦር ከራእየ ሲኖዳ ።
ከመ ይኩን ስምዓ በሳዕለ አሕዛብ ።
ባላመኑ በአሕዛብ መፈራረጃ ይሆንባቸው ዘንድ ።
ወይእተ አሚረ ይበጽሕ ሕልቀት ።
ያልተያያዘ ይእተ አሚረ ነው የሐሳዊ መሲሕን ሲናገር መጥቶ የጥጦስን ይእተ አሚረ አለ ነቢይ ኢሳይያስ የጼዋዌን ነገር ሲናገር መጥቶ የሚጠትን ይእተ አሚረ እንዳለ ።

፲፭ ወአምከመ ርኢክሙ ትእምርተ ርኩስ ዘም ዝባሬ ዘተብህለ በዳንኤል ነቢይ ዘይቀውም ውስተ መካን ቅዱስ ወዘያነብብ ለይለቡ ። ዳን ፱ ፤ ፳፯ ። ማር ፲፫ ፤ ፲፬ ።

፲፭ ሉቃ ፳፩ ፡ ፳ ። በቅዱስ ቦታ የሚቆም ማለት ለቤተ መቅደስ አንባቢነት የሚሾም ያስተ ውል ተብሎ የተነገረውን ቤተ መቅደስ በሚፈርስ በት ጊዜ የሚሆን የጥጦስን ጣዖቱን ያያችሁ እንደ ሆነ ያን ጊዜ ፍጻሜው ይመጣል ማለት የአይሁድ ጥፋት ይሆናል ትእምርተ በላዮር እንዲል። እንድም ቤተ መቅደስ በሚፈርስበት ጊዜ የሚሆን የጥጦስን ጣዖት ያያችሁ እንደሆነ ያን ጊዜ የአይሁድ ጥፋት ይሆናል ። ወዘተብህለ በዳንኤልም ለቤተ መቅደስ አንባቢነት የሚሾመው ለይለቡ ያለውን ያስተውል፤

እንድም ወይእተ አሚረ ያን ጊዜ የአይሁድ ጥፋት ይሆናል ። ወእምከመ ርኢክሙ ፡ ቤተ መቅደስ በሚፈርስበት ጊዜ የሚሆነን የጥጦስን ጣዖቱን ያያችሁ እንደሆነ ወዘተብህለ ። አሜሃ ይትኀተም ራእየ ነቢያት ወይትቀባዕ ቅዱስ ቅዱሳን ወየዓርፍ ሙስና ዲበ መትከፈ ርኩሳን ተብሎ በዳንኤል የተነገረውን ይወቅ።እንድም የተያያዘ ይእተ አሚረ ነው ሐሳዊ መሲሕን ሲናገር መጥቶ ምጽአትን ይእተ አሚረ አለ ለቤተ መቅደስ አንባቢነት የሚሾም ለይለቡ ተብሎ በዳንኤል የተነገረለትን ይህ ዓለም በሚያልፍበት ጊዜ የሚሆን የሐሳዊ መሲሕን ጣዖቱን ጣዖትነቱን ያያችሁ እንደሆነ ያን ጊዜ ኅልፈተ ዓለም ይሆናል ። እንድም ይህ ዓለም በሚያልፍበት ጊዜ የሚሆን የሐሳዊ መሲሕን ጣዖትነቱን ጣዖቱን ያያችሁ እንደሆነ ኅልፈተ ዓለም ይሆናል፤ ወዘተብህለ በዳንኤልም ለይለቡ ተብሎ የተነገረለትን ያስተውል ። እንድም ወይእተ አሚረ ያን ጊዜ ኅልፈተ ዓለም ይሆናል ። ወእምከመ ርኢክሙ ፡ ይህዓለም በሚያልፍበት ጊዜ የሚሆን የሐሳዊመሲሕ ጣዖቱን ጣዖትነቱን ያያችሁ እንደሆነ ዘተብህለ ፡ አሜሃ ይትኀተም ራእየ ነቢያት ወይትቀባዕ ቅዱሰ ቅዱሳን ወየዐርፍ ሙስና ዲበ መትከፈ ርኩሳን ተብሎ በዳንኤል የተነገረውን ያስተውል ። ወእምከመ ርኢክሙ ኃሣር ለሙስና ይላል በማርቆስ ።

፲፮ አሜሃ እለ ውስተ ይሁዳ ይጒዩ ውስተ አድባር ።

፲፮ ያን ጊዜ በይሁዳ ዕፃ ያሉ ወደ ተራራ ይሸሻሉ ።

፲፯ ወዘሂ ሀሎ ውስተ ናህስ ኢይረድ ይንሣእ ዘውስተ ቤቱ ።

፲፯ ከሰገነት የወጣም ከምድር ቤት ያለውን ያነሣ ዘንድ ወደ ምድር ቤት አይወርድም ።

፲፰ ወዘሂ ገዳመ ሀሎ ኢይትመየጥ ድኅሬሁ ይንሣእ ልብሶ ።

፲፰ በበረሀም ያለ ልብሱን ያነሣ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስም እንደ ወጣ ይቀራል ማለት ነው ።

፲፱ ወባሕቱ አሌሎን ለጽንሳት ወለእለ የሐፅና በውእቱ መዋዕል ።

፲፱ ነገር ግን በዚያ ወራት ለፀነሱ ወልደው ለሚያሳድጉ ሴቶች ወዮላቸው ። ሐተታ የፀነሱት ከመንገድ ይወልዳሉ የወለዱት ወተት ፍትፍት አምጡ ብለው ያስቸግሯቸዋልና ።

፳ ወጸልዩ ባሕቱ ከመ ኢይኩን ጕያክሙ በክረምት ወበሰንበት ግብ ፩ ፡ ፲፬ ።

፳ ነገር ግን ስደታችሁ በክረምት በሰንበት እንዳይሆንባችሁ ለምኑ ። ሐተታ ፡ ክረምት ላዩ ውኃ ታቹ ውኃ ነው አያሸጋግርምና በሰንበትም ዕለተ ጽርዓት ነው ። መንገድ ቅሉ የሚያሳይ አይገኝምና ። እንድም ሦስት ወር ክረምት ዐርፋለሁ ብሎ ዘጠኝ ወር ምግቡን ሲሰበስብ ይባጃል በ፯ኛው ቀን አርፋለሁ ብሎ ፮ቱን ቀን በተግባር ይሰነብታል ዐርፋለሁ ባለበት ጊዜ ስደት የመጣ እንደሆነ ከቀቢጸ ተስፋ ይደርሳልና እንድም አሜሃ እለ ውስተ ይሁዳ ብለህ መልስ በሃይማኖት ያሉ ሰዎች ረድኤተ እግዚአብሔርን ጥግ ያደርጋሉ ወዘሂ ውስተ ናሕስ ልዕልና ነፍስ ያለውም ወደ ትሕትና አይወርድም ይንሣእ ዘውስተ ቤቱ ሥጋዊ ሥራ ይሠራ ዘንድ ፡ ወዘሂ ሀሎ ገዳመ ፡ የመነነም ወደ ዓለም አይመለስም ይንሣእ ልብሶ ፡ ዓለማዊ ሥራ ይሠራ ዘንድ ፡ ወባሕቱ አሌሎን ለዕኑሳት ነገር ግን በዚያ ወራት ኃጢአትን በሐልዮ ፀንሰው በነቢብ ወልደው በገቢር ለሚያሳድጉ ሰዎች ወዮላቸው መከራ ነፍስ አለባቸውና እንድም ምእመናንን በትምህርት ፀንሰው በትምህርት ወልደው በትምህርት የሚያሳድጉ መምህራን ወዮላቸው መከራ ሥጋ አለባቸውና ፡ ወጸልዩ ባሕቱ ፡ ነገር ግን በሃይማኖት ብቻ ሳላችሁ ምግባር ሳትሠሩ ሞት እንዳይታዘዝባችሁ ለምኑ ። ክረምት ወርኃ ልምላሜ ነው ፍሬ የለውም ሰንበትም ዕለተ ጽርዓት ናትና በጽርዓት ሳላችሁ ሲል ነው ።

፳፩ እስመ ይከውን ይእተ አሚረ ዓቢይ ሕማም ወምንዳቤ ዘኢኮነ ከማሁ እምፍጥረተ ዓለም እስከ ዮም ።

፳፩ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ተደርጎ የማያውቅ ። ወኢይከውንሂ ። ከእንግዲህም ወዲህ የማይደረግ መከራ ጸዋትወ መከራ ያን ጊዜ ያደረጋልና ።

፳፪ ወሶበ ኢሐፀራ እማንቱ መዋዕል እምኢ ድኅነ መኑሂ ዘሥጋ ።

፳፪ ቀንስ ባያጥር ሥጋዊ ደማዊ ሰው ሁሉ ከመከራ ከከህደት ባልዳነም ነበር ። ወባሕቱ በእንተ ኅሩያኒሁ የሐፅራ እማንቱ መዋዕል ነገር ግን ስለ ምእመናን ቀኑ ያጥራል ። ከመዓልቱ አራት ከሌሊቱ አራት ሰዓት ይነሣለታል።

፳፫ አሜሃ እመቦ ዘይቤለክሙ ነዋ ዝየ ሀሎ ክርስቶስ ። ማር.፲፫ ፡ ፳፩ ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫ ።

፳፫ ያን ጊዜ ክርስቶስ ከወዲህ አለ ከወዲያ የለም ከወዲህ ወዲያ ይሄዳል ።
ወነዋ ከሀከ ፡

ከወዲያ አለ ከወዲህ የለም ከወዲያ ወዲህ ይመጣል ቢሏችሁ ።
ኢትእመኑ ።
በጅ አትበሉ ።

፳፬ እስመ ይትነሥኡ ሐሳውያን መሲሕ ፡
፳፬ መሲሕ ክርስቶስን የሚያሳብሉ በመሲሕ በክርስቶስ የሚያብሉ ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉና ።
ወሐሳውያን ነቢያት ፡
መምህራንን የሚያሳብሉ በመምህራን የሚያብሉ ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉና ወይገብሩ ተአምራተ ወመንክራተ ዓበይተ ለአስሕቶ ፡ ሰውን ለማሳት በምትሐት ድጋግ ተአምራት ያደርጋሉ ፡ እንድም ከመ ያስሕቱ ይሳል ፡ ያስቱ ዘንድ ፤
ሶበሰ ይትክሀሎሙ ለኅሩያንሂ እምአስሀትዎሙ ፡ አይቻላቸውም እንጂ ቢቻላቸውስ ምእመናንንም ባሳቷቸው ነበር ።

፳፭ ወናሁ አቅደምኩ ነጊሮተክሙ ፤
፳፭ እነሆ አስቀድሞ ነገርኋችሁ ፡
፳፮ እመቦ ዘይቤለክሙ ነዋ ገዳመ ሀሎ ኢትፃዑ ፤
፳፮ ክርስቶስ በገዳም ኅብስት አበርክቶ ያበላል ቢሏችሁ አትውጡ ማለት በጅ አትበሉ ።
ወነዋ ውስተ እብያት ኢትእመኑ ።
እነሆ በምኵራብ ያስተምራል ቢሏችሁ በጅ አትበሉ

፳፯ እስመ ከመ መብረቅ ዘይወፅእ እምጽባሕ ወያስተርኢ እስከ ዓረብ ።

፳፯ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ እንዲታይ ።
ከማሁኬ ይከውን ምጽአቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው የወልደ ዕጓለ እመሕያው የክርስቶስ ምጽአቱ እንዲህ ነውና ማለት ሁሉ ያየዋልና ።
፳፰ ህበ ሀሎ ገደላ ህየ ይትጋብኡ አንስርት ። ሉቃ.፲፯ ፡ ፴፯ ።
፳፰ በአይቴ ንትራከብ ብለውታል በሉቃስ ያቀናዋል ምግብ ካለበት አንስርት ይሰበሰባሉ አለ እኔ ካለሁበት እናንተ ትሰበሰባላችሁ ። ሐተታ ፡ ገደላ አለው ራሱን ነፍስ የተለየችውን መለኮት የተዋሐደውን ሥጋውን ነውና የምንቀበለው ። አንስርት አላቸው ሐዋርያትን አንስርት ክንፍ አላቸው ። ሐዋርያትም ክንፈ ጸጋ አላቸውና ። አንስርት ተመስጦ እንዳላቸው ሐዋርያትም ተመስጦ አላቸውና ።

በእንተ ካልዓዊት ምጽአት ፤
ዘወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
፳፱ ወእምድኅረ ሕማሞን ለእማንቱ መዋዕል ፀሐይኒ ይፀልም ። ኢሳ.፲፫፡፲ ። ሕዝ.፴፪ ፡ ፯ ። ኢዩ ፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ፡ ማር.፲፫ ፡ ፳፬ ። ሉቃ ፳፩ ፡ ፳፭ ። ራዕ.፮ ፡ ፯ ።

፳፱ በሐሳዊ መሲሕ የሚደረገውን መናገር ነው ይህ ሁሉ መከራ ከተደረገ በኋላ ፀሐይ ያልፋል ።
ወወርኅኒ ኢይሁብ ብርሃና ፡ ጨረቃም ብርሃኑን አይሰጥም ማለት ያልፋል ።
ወከዋክብትኒ ይወድቁ እምሰማይ ። ከዋክብትም ያልፋሉ ወያንቀለቅል ኃይለ ሰማያት ፡ አድማስ ድንፁን ይለቃል ።

፴ ወይእተ አሚረ ያስተርኢ ትእምርቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ውስተ ሰማይ ።

፴ ያን ጊዜ የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ምልክቱ በሰማይ ይታያል አሥረ ርግዘቱን አሥረ ቅንዋቱን እስራቱን ሳያጠፋ ይመጣልና ። ታሪክ ሳባ ጳኩሚስ እንደታየው ሲሰግድ ወዙ ወርዶ መሬቱን ጭቃ አደረገው ወዲያው ጌታ ተገለጸለት አንተን አገኝ ብየ እንዲህ እደክማለሁ አለው እኔም እንጂ ሳንተ ብየ እንዲህ ሁኜ ተሰቅያለሁ ። ብሎ በዕለተ ዓርብ እንደ ተሰቀለ ሁኖ ጐኑን እንደ ተወጋ ደሙ እንደፈሰሰ ሁኖ ታይቶታል ። እንድም ወእምድኅረ ሕማሞን ብለህ መልስ ። በጥጦስ የሚደረገው መከራ ነው ። ይህ ሁሉ መከራ ካለፈ በኋላ ፀሐይ ይጨልማል ።

ወወርህኒ ኢይሁብ ብርሃና ወከዋክብትኒ ይወድቁ እምሰማይ ። ጨረቃ ይጨልማል ከዋክብትም ይወድቃሉ ፤ በዕለተ ዓርብ በሠሩት ኃጢአት እንደ ተፈረደባቸው ለማጠየቅ በዕለተ ዓርብ የተደረገው ሁሉ ተደርጓል ። ወይእተ አሚረ ያን ጊዜ የወልደ ዕጓለ እመሕያው የክርስቶስ ምልክቱ በሰማይ ይታያል ። ታሪክ ፡ በሮም አንጻርና በኢየሩሳሌም አንጻር ያሉ ከዋክብት ሠልፍ ሰርተው ሲዋጉ በሮም አንጻር ያሉት በኢየሩሳሌም አንጻር ያሉትን ድል ሲያደርጓቸው ታይተዋል ። ሮማውያን አይሁድን ድል ለማድረጋቸው ምሳሌ ነው ።
አሜሃ ይበክዩ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ሶበ ይሬእይዎ ለወልደ ዕጓለ ዕመሕያው እንዘ ይመጽእ በደመና ሰማይ ።
በሰማይ ደመና ማለት በባሕርይ ክብሩ ሲመጣ ባዩት ጊዜ ያን ጊዜ አሕዛብ ሁሉ ያዝናሉ ። ሐተታ የዕርገት የደብረ ታቦር የምጽአት ደመና የባሕርይ ክብር ነው ። እንድም በሥጋ ማርያም መጥቶ ባዩት ጊዜ ፡ ሰማይ ዳግሚት እንዲል እንድም በክበበ ትስብእት መጥቶ ባዩት ጊዜ ያዝናሉ ።
ምስለ ኃይል ።

ከኃይል ጋራ ማለት ዓለምን ከማሳለፍ ጋራ ።
ወስብሐት ብዙኅ ።
ቅዱስ እግዚአብሔር ዘያነቅሖሙ ለምውታን ተብሎ ከመመስገን ጋራ ሲመጣ ባዩት ጊዜ ።

፴፩ ወይፌንዎሙ ለመላእክቲሁ ምስለ ቃለ ቀርን ። ፩፡ቆሮ.፲፭ ፡ ፶፪ ። ፩፡ ተሰ ፣ ፬ ፡ ፲፮ ።

፴፩ ዐዋጅ ከመንገር ጋራ መላእክትን ያዛቸዋል ።
ወስብሐት ዓቢይ ።
ብርሃኑ መለኮቱን ገልጾ በመጣ ጊዜ ።
ወያስተጋብእዎሙ ለኅሩያኒሁ እም፬ቱ ነፋሳት እም አጽናፈ ሰማይ እስከ አጽናፊሃ ።
ሙታንን ከራቁ ማዕዘን ይሰበስቧቸዋል ። ይመጽእ ወያስተጋብእሙ ይፌንዎሙ ወያስተጋብእዎሙ ይላል ።

፴፪ ወእምዕፀ በለስ አእምሩ አምሳሊሁ ፤
፴፪ ነገሩን በበለስ ዕወቁ ።
እምከመ ለምለመ አዕጹቂሁ ወሠረጸ ቆጽሉ ተአምሩ ከመ ቀርበ ማዕረር ።
በለስ ቅጠሉ የለመለመ ዓጽቅ ያወጣ እንደሆነ መከር እንደ ደረሰ ዕወቁ ። ሐተታ ፣ የጥጦስን በቅጠል የሐሳዊ መሲሕን በአበባ የምጽአትን በፍሬ መስሎ ይናገራል ። አንድም እንደ ቅጠሉ ሐሳዊ መሲሕ ነግሦላቸው ቤተ አይሁድ ደስ ብሏቸዋል። እንደ አበባው የምእመናን መከራቸው እንደ ፍሬው ሞታቸው ፣ አንድም እንደ ፍሬ ሞታቸው እንደ አበባ ክብራቸው ። አንድም ቆጽል አይለወጥም ። እንደ አበባው የአይሁድ መከራቸው እንደ ፍሬው ሞታቸው ፤ አንድም እንዳበባው ሞታቸው እንደ ፍሬው ፍዳቸው ።

፴፫ ከማሁ አንትሙኒ እምከመ ርኢክሙ ዘንተ ኵሉ አእምሩ ከመ ቀርበ ኀበ ኆኅት ።

፴፫ እናንተም ይህን ሁሉ ያያችሁ እንደሆነ እንደቀረበ ከደጅ እንዳለ ዕወቁ ከደጅ የቆመ ፈጥኖ እንዲገባ ፈጥኖ እንዲደረግ ዕወቁ ማለት ነው ።

፴፬ አማን እብለክሙ ከመ ኢተኃልፍ ዛቲ ትውልድ እስከዝ ኵሉ ይትገበር ።
፴፬ ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ቤተ አይሁድ ኢታልፍም ብየ እንዳታልፍ እነግራችኋለሁ ።
፴፭ ሰማይ ወምድር የኃልፍ ማር.፲፫፣፴፩ ።
፴፭ ሰማይና ምድር ያልፋል ። ወቃልየሰ ኢየኃልፍ ።
ሕጌ ግን አያልፍም ። አንድም አለፍ ያልሁት ያልፋል አለፍ ያላልሁት አያልፍም ። አንድም ሕጌን የያዘ አያልፍም ሕጌን ያልያዘ ግን ያልፋል ።
ከመ ይደልዎ ተጊሀ ለክርስቲያን እስመ ኢየአምር ሰዓተ ሞቱ ።

፴፮ ወበእንተሰ ይእቲ ዕለት ወይእቲ ሰዓት አልቦ ዘየአምራ ።

፴፮ ያችን ዕለት ያችን ሰዓት የሚያውቃት የለም ። ይእቲ ባለው ወኪያሃ ይላል አብነት ወይእቲ ማለት ነው።ወሰምዓት ዮዲት በኪያሆን መዋዕል እንዲል ። ሐተታ ፣ ዘመኑ ዘመነ ዮሐንስ ወርኁ ወርኃ መጋቢት ዕለቱ ዕለተ እሑድ ሰዓቱ መንፈቀ ሌሊት አይደለም ቢሉ ብዙ ዘመነ ዮሐንስ ብዙ ወርኃ መጋቢት ብዙ ዕለተ እሑድ ብዙ መንፈቀ ሌሊት አለና ።
ኢመላእክተ ሰማይ ።
መላእክትም ሆነው ።
ወኢወልድ ።
ደቂቀ አዳምም ሁነው አያውቋትም ። ኦሪት ዘሌደት እንዲል ዘእንበለ አብ ባሕቲቱ ።
ክብቻው ከአብ በቀር አብ ብቻ ያውቃታል እንጂ ሐተታ ከፍጡራን ሲለየው ነው እንጂ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ሲለየው አይደለም ። አንድም ወልድ ቅድመ ተዋሕዶ የነበረ ዐላዋቂ ሥጋን እንደ ተዋሐደ ሰማጠየቅ ። እኮ ኢያእሚሮ ኀቡእተ አላ ከመ የሀብ መካነ ለጥንተ ትስብእቱ ዘኢየአምር ኀቡእተ እንዲል ። አንድም አብ ለልጁ በመስጠት ዐውቋታል ፣ ወልድ ግን በሥራ ዐላወቃትም ሲል እንዲህ አለ ፣ አንድም ፣ ኢወልድ ባሕቲቱ ዘእንበለ አብ ፣ ወልድ ብቻ ያለ አብ አያውቃትም ።

፴፯ ወበከመ ኮነ በመዋዕሊሁ ለኖኅ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ዘፍ ፣ ፯፣ ፯ ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፳፯ ።

፴፯ በኖኅ ዘመን እንደተደረገው የወልደ ዕጓለ እመሕያው የክርስቶስ ምጽአቱ እንዲህ ይደረጋል።

፴፰ እስመ በከመ ኮነ በመዋዕለ ኖኅ እምቅድመ ማየ አይህ ይበልዑ ወይሰትዩ ።

፴፰ ከማየ አይህ አስቀድሞ ሲበሉ ሲጠጡ ያወስቡ ወይትዋሰቡ ።
ሲያገቡ ሲጋቡ እንደነበረ ።
እስከ አመ ቦአ ኖኅ ውስተ ንፍቀ ታቦት ።
ንፍቀ ታቦተ ሲል ነው ስጠተ ልብሰ ጠፈረ ቤት እንዲል ስጡጠ ልብሰ ጥፉረ ቤተ ሲል ኖኅ ክፍል ክፍል ካለው መርከብ እስቲገባ ድረስ ።

፴፱ ወኢያእመሩ እስከ አመ መጽአ ማየ አይኅ ወአጥፍአ ኵሎ ፤
፴፱ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስኪያጠፋ ድረስ እንዳላወቁ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

የክርስቶስ ምጽአቱ እንዲህ ነውና በኖኅ ጊዜ እንደ ተደረገ ይደረጋል ።

፵ አሜሃ ፪ቱ ይሄልዉ ውስተ ፩ዱ ገራኅት ።
፵ ያን ጊዜ ሁለት ሰዎች ባንድ እርሻ ይኖራሉ
፵፩ ፩ደ ይነሥኡ ።
፵፩ አንዱን በሞት ይወስዳሉ ።
ወካልዖ የኃድጉ ።
አንዱን በሕይወት ይተዋሉ ።
ወ፪ቲ የሐርፃ በ፩ዱ ማኅረፅ ሁለት ሴቶች ባንድ ወፍጮ ይፈጫሉ ። ሐተታ ተራ አንድም ሽርሞ አንድም መቀበያውን አንድ አድርገው ።
አሐተ ይነሥኡ ።
አንዲቱን በሞት ይወስዳሉ ።
ወካልዕታ የኃድጉ ።
አንዲቱን ይተዋሉ ።
፪ቱ ይሰክቡ ውስተ ፩ዱ አራት ባልና ሚስት ባንድ አልጋ ይተኛሉ ።
፩ደ ይነሥኡ ።
አንዳቸውን በሞት ይወስዳሉ ።
ወካልዖ የኃድጉ ።

አንዳቸውን በሕይወት ይተዋሉ አንድም ፪ቱ ይሄልዉ ብለህ መልስ ለያርኅብ እግዚአብሔር ምድር ለያፌት እንዲል ። በያፌት ዕፃ ፪ ሰዎች ይኖራሉ ምግባር ሃይማኖት የያዘውን ይነሥኡ ወደ ገነት ። ምግባር ሃይማኖት ያልያዘውን የኀድጉ በገሃነም ። ወ፪ቱ ይሰክቡ ውስተ ፩ዱ አራት ። ለይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ቤቱ ለሴም እንዲል በሴም ዕፃ ፪ ሰዎች ይኖራሉ፤ምግባር ሃይማኖት የያዘውን ወደገነት ያልያዘውን ወደ ገሃነም ይተዋሉ ። አንድም ፪ቱ ይሄልው ብለህ መልስ ባሕታውያን በበረሃ ይኖራሉ እንደ እንጦንስ እንደ መቃርስ እንደ አቡነ ተክለሃይማኖት ያሉትን ይነሥኡ ወደ ገነት ። እንደ ሡናየ ዝክር እንደ በዓለ መቅጹት ያሉትን የኃድጉ በገሃነም ።
ወ፪ቲ የሐርጻ ።

ነዳያን በዚህ ዓለም ይኖራሉ እንደ አልዓዛር እንደ ሐዋርያት ያሉትን ወደገነት ። እንደ ይሁዳ እንደ አይሁድ ያሉትን በገሃነም ። ወ፪ቱ ይሰክቡ ውስተ ፩ዱ አራት ፣ ባለጸጎች በዚህ ዓለም ይኖራሉ ፣ እንደ ኢዮብ እንደ አብርሃም ያሉትን ይነሥኡ ወደገነት፣ እንደ ነዌ እንደ ኪራም ያሉትን የኀድጉ በገሃነም።

፵፪ ትጉሁ እንከ እስመ ኢተአምሩ በዓይ ሰዓት ይመጽእ እግዚእክሙ ማር ፣ ፲፫ ፣ ፴፫ ።
ሉቃ ፣ ፲፪ ፣ ፴፱

፵፪ ጌታችሁ በማናቸውም ሰዓት እንዲመጣ እታውቁምና ለትሩፋት ተግታችሁ ኑሩ ።
፵፫ ወዘንተ ባሕቱ አእምሩ ወኢትርስው ።
፵፫ ባሕቱ ዋዌ ነው ይህንም ዕወቁ ስበሁ የእምር በዓለ ቤት ጊዜ ይመጽእ ሠራቂ እምተግሀ ወእምሀለወ ።

ባለቤት ሌባ የሚመጣበትን ጊዜ ቢያውቅ ተግቶ በጠበቀ ነበር ።
ወእምኢኃደገ ይክርዩ ቤቶ ።
ግድግዳውን ምሰው ናሱን አፍርሰው ይሰርቁት ዘንድ ቸል ባላለም ነበር ።

፵፬ ወበእንተዝ እንትሙኒ ድልዋኒክሙ ሀልዉ እስመ በጊዜ ኢተኃዘብክሙ ይመጽእ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

፵፬ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ባልጠረጠራችሁት ዕለት ባላወቃችሁት ሰዓት ይመጣልና እንደዚህ እናንተም ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ።

፵፭ መኑ እንጋ ውእቱ ገብር ምእመን ጠቢብ ዘይሠይሞ እግዚኡ ውስተ ኵሉ ቤቱ ።

፵፭ ቅዱስ ጴጥሮስ ለነሁ ትሜህረነ ወሚመ ለኵሉ ብሎታል በሉቃስ ፣ ምን እናንተን ብቻ እናንተን ለመሰለ ሁሉ ነው እንጂ ብሎ አያይዞ በዚያ ውስ ላይ ጌታው አምኖ የሚሾመው ብልህ በጎ ባሪያ ማነው ።
ከመ የሀቦሙ ሲሳዮሙ በበጊዜሁ ።
በየጊዜው ምግባቸውን ይሰጣቸው ዘንድ የዕለት የሳምንት የወር ያመት ምግቡን የሚቀበል አለና፤

፵፮ ብፁዕ ውእቱ ገብር ዘመጺአ እግዚኡ ይረክቦ እንዘ ከመዝ ይገብር ። ራዕ ፣ ፲፮ ፣ ፲፭ ።

፵፮ ጌታው በመጣ ጊዜ እንዲህ ሲያደርግ ማለት ምግባቸውን ሲሰጣቸው የሚያገኘው ባሪያን ዑድ ክቡር ነው ።

፵፯ አማን እብለክሙ ከመ ዲበ ኵሉ ጥሪቱ ይሠይሞ ።

፵፯ በገንዘቡ ሁሉ ይሾመዋል ብየ እንዲሾመው በውነት እነግራችኋለሁ ።

፵፰ ወእመሰ ይቤ ውእቱ ገብር እኩይ ይጐነዲ እቲወ እግዚእየ ።

፵፰ ያ ክፉ ባሪያ ግንጌታዬ የሚመጣበት ጊዜ ገና ነው ብሎ ።
፵፱ ወይዘብጥ አብያጺሁ አግብርተ ይበልዕ ወይስቲ ምስለ ሰካርያን ።
፵፱ የጌታውን ባሮች ባልንጀሮቹን ቢመታ ማለት በበትረ ረኃብ ቢመቱ ካዝማሪ ከዘዋሪ ጋራ እየበላ እየጠጣ ምግባቸውን አልሰጥም ቢል ።
፶ ወይመጽእ እግዚኡ ለውእቱ ገብር በዕለተ ኢተሀዘበ ወበጊዜ ኢያእመረ ወይሠጥቆ እማእከሉ
፶ ባላወቀው ዕለት ባልጠረጠረው ሰዓት መጥቶ ጌታው ከሹመቱ ይሽረዋል ።
፶፩ ወይሬሲ መክፈልቶ ምስለ መደልዋን ኀበ ሀሎ ብካይ ወሐቅየ ስነን ። ማቴ ፣ ፲፫ ፣ ፵፪፡፳፭፡፶፩።

፶፩ ዕድል ፈንታውን ጽዋ ተራውንም ልቅሶ ጥርስ ቁርጥማት ካለበት ቦታ ከግብዞች ጋራ ያደርግበታል ። አንድም መኑ ውእቱ ብለህ መልስ ። ጌታው አምኖ በነዳያን ላይ የሚሾመው ባለጸጋ ማነው ጌታ ለሰው ብዕል መስጠቱ ለነዳያን መሾሙ ነውና ከመ የሀቦሙ ስጠን ባሉት ጊዜ ለነዳያን ሲሰጣቸው ። ብፁዕ ውእቱ ጌታው በመጣ ጊዜ ለነዳያን ምግባቸውን ሲሰጣቸው የሚገኝ ባለጸጋ ንዑድ ክቡር ነው ። አማን እብለክሙ በወዲያውም ዓለም ብዕል ይሾሙዋል ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ። ወእመሰ ይቤ ያ ክፉ ባለጸጋ ግን የምሞትበት ጊዜ ገና ነው ብሎ ካዝማሪ ከዘዋሪ ጋራ እየበላ እየጠጣ ነዳያን በበትረ ረኃብ ሲሞቱ አልሰጥም ቢል ዘበ ይዳደቅ በእናቅጽ ውእቱኬ ያመነድብ ነፍሳተ እንዲል ወይመጽእ እግዚኡ ፤ ባልጠረጠረው ዕለት ባላወቀው ሰዓት ጌታው መጥቶ በማእከለ ዘመኑ ነፍሱን ከሥጋው ይለያታል እድል ፈንታውን ጽዋ ተራውን ከኃጥአን ጋራ ጽኑዕ ሥቃይ ባለበት ቦታ በገሃነም ያደርግበታል ። አንድም መኑ ውእቱ ብለህ መልስ ፤ ጌታው አምኖ በምእመናን የሚሾመው ቄስ መምር ማነው ። ከመ የሀቦሙ ሲሳዮሙ ፤ ያስተምራቸው ዘንድ ንስሐን ሥጋውን ደሙን ይሰጣቸው ዘንድ ። ብፁዕ ውእቱ ጌታው በመጣ ጊዜ ሲያስተምራቸው የሚገኝ መምህር ንስሐን ሥጋውን ደሙን ሲሰጣቸው የሚገኝ ቄስ ንዑድ ክቡር ነው ። አማን ዕብለክሙ በወዲያው ዓለም ምሥጢር ክብር ይሾመዋል ብዬ እንዲሾመው በውነት እነግራችኋለሁ ። ወእመሰ ይቤ ውእቱ ገብር እኩይ ። ያ ክፉ መምር ቄስ ግን የምሞትበት ጊዜ ገና ነው ብሎ ። ወይዘብጥ አብያጺሁ ምእመናን በበትረ ክህደት ሲሞቱ አላስተምርም ቢል በበትረ ኃጢአት ሲሞቱ ንስሐን ሥጋውን ደሙን አልሰጥም ቢል ። ኢትዘበጥ አንተ ከመ ኢይደላሁ አነ ዛቲ ምጽንጋዕ ምዕረ ትዘብጠኒ ወምዕረ ትዘብጠኒ እንዲል። ወይመጽእ እግዚኡ።ባላወቀው ዕለት ባልጠረጠረው ሰዓት ጌታው መጥቶ ነፍሱን ከሥጋው ይለያታል ። ወይሬሲ መክፈልቶ ፤ እድል ፈንታውን ጽዋ ተራውንም ከኃጥአን ጋራ ጽኑ ሥቃይ ባለበት በገሃነም ያደርግበታል ።

በእንተ ደናግል ጠባባት ወአብዳት ።

ምዕራፍ ፳፭ ።

፩ አሜሃ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ዐሥሮን ደናግለ እለ ነሥአ መኃትዊሆን ወወፅአ ውስተ ቀበላ መርዓዊ ።

፩ አብነት አሜሃ ይእተ አሚረ ይላል ያን ጊዜ መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ። ሕገ ወንጌል ተስፋ ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ፋና ይዘው ዐሥሩ ደናግል ሊቀበሉት የወጡ ሙሽራን ትመስላለች ። አንድም መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ትመስል መኃትወ መርዓዊን ሲቀበሉ ፲ ደናግል ይዘውት የወጡ ፋናን ትመስላለች ። አንድም መንግሥተ ሰማይ ምእመናን ትመስል ዐሥሮን ደናግለ ። ሙሽራውን ለመቀበል ፋና ይዘው የወጡ ደናግልን ትመስላለች ሐተታ ደናግል አላቸው ምእመናንን ፤ ድንግል ባባት በናቷ ቤት ሳለች ኋላ ከባሏ ጋራ አንድ የምትሆንበትን ሥራ ስትማር እንድታድግ ምእመናንም በዚህ ዓለም ሳሉ ኋላ ከክርስቶስ ጋራ አንድ የሚሆኑበትን ሥራ ሲሠሩ ይኖራሉ።አንድም በተፈጥሮ ደናግል ናቸውና አንድም ድንግልና ሥጋ አላቸውና ይህስ ለሁሉ አይቻልም ብሎ ድንግልና ነፍስ አላቸውና ።

፪ ወኃምስ እምኔሆን አብዳት አማንቱ ።

፪ ካሥሩ አምስቱ ሰነፎች ናቸው ወኃምስ ጠባባት ።
አምስቱ ልባሞች ናቸው ።

፫ ወዓብዳትሰ ነሚአን መኃትዊሆን ኢነሥአ ቅብዓ ምስሌሆን ።

፫ ሰነፎች ፋና ይዘው በማሰሮቻቸው ዘይት አልያዙም ።

፬ ወጠባባትሰ ነሥአ ቅብዓ ምስለ መኃትዊሆን በገማዕዊሆን ።

፬ ልባሞች ግን ከፋናቸው ጋራ በማሰሮቻቸው ዘይት ይዘዋል ሐተታ፤ ዓብዳት የሚላቸው ሃይማኖት ጾም ጸሎት ትሕትና ኃፊረ ገጽን ይዘው ፭ኛ በልቡናቸው ፍቅርን ያልያዙ ናቸው።ኃፊረና ገጽና ትሕትናስ አንድ ወገን ናቸው ብሎ ሃይማኖት ጾም ጸሎት ትሕትና ኃፊረ ገጽ አንድ ወገን ንጽሕናን ይዘው ፭ኛ በልቡናቸው ፍቅርን ያልያዙ ናቸው ። ጠባባት የሚላቸው አምስቱን ይዘው ስድስተኛ በልቡናቸው ፍቅርን የያዙ ናቸው ። ቅብዕ ኢይርኀቅ ቅብዕሰ ፍቅረ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው እንዲል ። አምስቱን ይዛችሁ ስድስተኛ በልቡናችሁ ፍቅርን ካልያዛችሁ አይሆንም ይሏችዋል ከነግህ ከሠለስትእንይዛለን ሲሉ ሞት ይመጣባቸዋል ። እኒያ አለመጠቀማቸውን እነዚህ መጠቀማቸውን መናገር ነው ።

፭ ወጐንድዮ መርዓዊ ደቀሰ ኵሎን ወኖማ ።

፭ ሙሽራው በዘገየ ጊዜ ዓብዳትም ጠባባትም ተኙ ።

፮ ወከዊኖ መንፈቀ ሌሊት ውውዓ ኮነ ናሁ መርዓዊ መጽአ ፃዑ ተቀበሉ ።

፮ መንፈቀ ሌሊት ሲሆን ሙሽራው መጥቷልና ወጥታችሁ ተቀበሉ ተብሎ ተነገረ ። ሐተታ ፤ በሀገራቸው ሙሽራ የሚመጣ በመንፈቀ ሌሊት ነውና ።

፯ ወእምዝ ነቅሐ እልኩ ደናግል ኵሎን ወአሠነያ መኃትዊሆን ወወፅአ ውስተ ቀበላ መርዓዊ

፯ ከዚህ በኋላ ልባሞች ተነሥተው ፋናቸውን አዘጋጅተው ሙሽራውን ሊቀበሉ ወጡ ።

፰ ወእልኩ ዓብዳት ይቤላሆን ለጠባባት ሀባነ ቅብዓ እምቅብዕክን ።

፰ ሰነፎች ልባሞችን ከዘይታችሁ ዘይት ስጡን አሏቸው ።
እስመ መኅትዊነ ጠፍአነ ፤ ዘይት አልቀብናልና ።

፱ ወአውሥአሆን ጠባባት እንዘ ይብላ አልቦ ዘየአክል ለነ ወለክን ።

፱ ልባሞች ለኛና ለናንተ የሚበቃ ዘይት አልያዝንምና ፥ አላ ሑራ ወተሣየጣ ለክን እምኀበ እለ ይሠይጡ ።

፲ ሄዳችሁ ዘይት ከሚሸጡ ግዙ እንጂ አሏቸው ወሐዊሮን ይሣየጣ በጽሐ መርዓዊ ።
፲ ለጊዜው ሂደው ሳሉ ሙሽራው መጣ ።
ወቦአ ምስሌሁ እልኩ እለ ድልዋት ውስተ ከብካብ ።
የተዘጋጁ ከሱ ጋራ እንደሱ ወደሰርግ ገቡ ።
ወተዐፅወ ኆኅት ፤ ደጅ ተዘጋ ፤

፲፩ ወድኅረ መጽአ እልኩሂ ደናግል ወይቤላ እግዚኦእግዚኦ አርኅወነ ።

፲፩ እነዚያ ከገቡ ደጅ ከተዘጋ በኋላ ሰነፎች መጥተው ክፈትልን ማለት እንድንገባ አድርገን አሉት ።

፲፪ ወአውሥአን ፤ መለሰላቸው ወይቤሎን አማን እብለክን ከመ ኢየአምረክን ።

፲፪ ዐላውቃችሁም ብየ እንዳላውቃችሁ በውነት እነግራችኋለሁ እስመ ስእንክን ተጊሃ ወእምስዮ አሐተ ሰዓተ ምስሌየ ። ተግታችሁ ሥራ አልሠራችሁም ከኔ ጋራ አንዲት ሰዓት መቆ ምመቆየት አልተቻላችሁምና ።

፲፫ ትግሁኬ እስመ ኢተአምሩ ዕለታ ወሰዓታ እንተ ባቲ ይመጽእ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ማር. ፲፫ ፥ ፴፫ ።

፲፫ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ የሚመጣበትን ዕለት ሰዓት አታውቁምና ለትሩፋት ተግታችሁ ኑሩ ። አንድም ወኰንድዮ መርዓዊ ብለህ መልስ ምጽአት በዘገየ ጊዜ ምእመናን ሁሉ መሞታቸውን መናገር ነው ። ወከዊኖ መንፈቀ ሌሊት በማእከለ ዘመን መርዓዊ ክርስቶስ መጥቷልና ለተዋሕዶ የሚያበቃ ሥራ ሥሩ ተብሎ ተነገረ ። ሐተታ ያልተካከለ መንፈቅ ነው ወንፍቃ ለሌሊት ወመንፈቆሙ ናፈቁ እንዲል ። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት ያለውን አንድ ወገን ፥ ከምጽአት በኋላ ያለውን አንድ ወገን አድርጎ መንፈቅ አለ ። አንድም የተካከለ መንፈቅ ነው ዓለም ሳይፈጠር ያለውንና ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለውን አንድ ወገን ከምጽአት በኋላ ያለውን አንድ ወገን አድርጎ ተናገረ የዚያ ጥንቱ እንዳይታወቅ የዚህም ፍጻሜው አይታወቅምና ፥ የቍጥር መጽሐፍ ክፍል ዳግም መንፈቅ ይላል ተአምረ ኢየሱስ ወበ፮ ሰዓተ ሌሊት ተንሥአ እግዚእ ኢየሱስ ይላልሳ ቢሉ ሦስት ሰዓት አሳልፎ ነው መከራ መቀበል የጀመረ ፥ ከዚያ ተነሥቶ ቈጥሮ ፮ አለ እንጂ ፥ ልደቱም ጥምቀቱም ትንሣኤውም ምጽአቱም ባሥረኛው ሰዓት ነው ። ወእምዝ ተንሥአ ለተዋሕዶ የሚያበቃ ሠርተው ሀባነ ቅብዓ ከሥራችሁ አትርፉልን እስመ መኅትዊነ ጠፍአነ ለተዋሕዶ የሚያበቃ ሥራ አልሠራንምና ማለት ባንዱ ሥራ አንዱ የሚጠቀም እንደመሰላቸው መናገር ነው ፥ ወአውሥአሆን እንዘ ይብላ አልቦ ዘየአክል ለነ ወለክን ፥ ለኛና ለናንተ የሚያበቃ ሥራ የለንም አሏቸው ማለት ፥ ባንዱ ሥራ አንዱ እንዳይጠቀም ማወቃቸውን መናገር ነው ፥ አላ ሑራ ፥ ምሕረትን ከሚያድሉ ከሥላሴ ምሕረትን ከሚያሰጡ ከነዳያን ለምኑ እንጂ አሏቸው ፤ ወሐዊሮን ይሣየጣ ፥ ነግ ሠልስት ሥራ እንሠራለን ሲሉ ምጽአት ደረሰ ። ወቦአ ምስሌሁ ፥ ሥራ ሠርተው የተገኙት ተዋሐዱት ተዋሐዳቸው ። ወተዐፅወ ኆኅት ምሕረት ተከለከለ ፥ ወድኅረ መጽአ ወይቤላ አርኅወነ የሚገቡ እንደመሰላቸው መናገር ነው ወአውሥአን አላውቃችሁም ብየ እንዳላውቃችሁ በውነት እነግራችኋለሁ ፥ ፈጥሮስ ዐላውቃችሁም ማለት አይመችም ብሎ ወለድኳችሁ ኪድኳችሁ እላችዋለሁ ። እስመ ስእንክን ተጊሃ ፥ ለተዋሕዶ የሚያበቃ ሥራ አልሠራችሁምና ትግሁኬ እንዳለፈው ፥ ሐተታ ዓብዳት የሚላቸው ሃይማኖት እንበለ ምግባር ንጽሐ ሥጋ እንበለ ንጽሐ ነፍስ ፍቅር እንበለ ተስፋ ምሕረት እንበለ ትዕግሥት ጸሎት ዘምስለ ትምክህት የያዙ ናቸው ። ጠባባት የሚላቸው ሃይማኖት ዘምስለ ምግባር ንጽሐ ሥጋ ዘምስለ ንጽሐ ነፍስ ፥ ምሕረት ዘምስለ ትዕግሥት ፍቅር ዘምስለ ተስፋ ጸሎት እንበለ ትምክህት የያዙ ናቸው ይህን ይዛችሁ ይህን ካልያዛችሁ አይሆንም ይሏቸዋል ። ከነግ ከሠልስት እንይዛለን ሲሉ ሞት ይመጣባቸዋል እኒህ መጠቀማቸውን እኒያ አለመጠቀማቸውን መናገር ነው ። አንድም ዓብዳት የሚላቸው አእምሮ ለብዎ ሰሚዕ ምሕረት ትዕግሥት እኒህን ኃምስቱን ይዘው አሚን ተስፋ ፍሥሐ ሰላም ፍቅርን ያልያዙ ናቸው ጠባባት የሚላቸው ዓሥሩንም የያዙ ናቸው ይኸን ይዛችሁ ይኸን ካልያዛችሁ አይሆንም ይሏቸዋል ። ከነግ ከሠልስት እንይዛለን ሲሉ ሞት ይመጣባቸዋል እኒህ መጠቀማቸውን እኒያ አለመጠቀማቸውን መናገር ነው ። እንድም ዓብዳት የሚላቸው አይሁድ ተንባላት ናቸው ፥ ጠባባት የሚላቸው ክርስቲያን ናቸው ካላመናችሁ ካልተጠመቃችሁ አይሆንም ይሏቸዋል ከነግ ከሠልስት እንጠመቃለን ሲሉ ሞት ይመጣባቸዋል እኒህ መጠቀማቸውን እኒያ አለመጠቀማቸውን መናገር ነው ።
አንድም ዓብዳት የሚላቸው አምነው ተጠምቀው የክርስቲያን ሥራ የማይሠሩ ናቸው ጠባባት የሚላ

ቸው አምነው ተጠምቀው ሥራ የሚሠሩ ናቸው አምናችሁ ተጠምቃችሁ ሥራ ካልሠራችሁ አይሆ ንም ይሏቸዋል ከንግ ከሠልስት እንሠራለን ሲሉ ሞት ይመጣባቸዋል እኒህ መጠቀማቸውን እኒያ አለመጠቀማቸውን መናገር ነው ፡፡

በእንተ ምሳሌ ዘመካልይ ፡፡

፲፬ እስመ ከመ ብእሲ ዘይነግድ ወጸውዓ አግብርቲሁ ወመጠዎሙ ንዋዮ ይትገበሩ ቦቱ፤ ሉቃ ፲፱ ፲፪ ፡፡

፲፬ መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ፡ ሕገ ወንጌል ተሰፋ ተሰፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ብላቴኖችን ጠርቶ ወጥተው ወርደው ያተርፉበት ዘንድ ገንዘቡን የሰጣቸውን ነጋዴን ትመስላለችና ትገሥ ፣ እንድም ትመስላለችኮን ፡፡

፲፭ ዐ ለዘወሀበ ፭ተ መክሊተ ፡፡
፲፭ አምስት መክሊትን ለሰጠው ሰው አም ስት መክሊት አለው አምስት መክሊትን ለሰጠው ሰው ስጦታ አለው ለሰጠው አምስት መክሊት አለው አምስት መክሊት የሰጠው ሰው አለ ፡፡
ወዐ ለዘወሀበ ፪ተ መክሊተ ፡፡ ሁለት መክሊት የሰጠው ሰው አለ እንዳለፈው በል ፡፡
ወዐ ለዘወሀበ አሐደ መክሊተ ፣ አንድ መክሊት የሰ ጠው ሰው አለ ፡፡
ወለለ፩ዱ እምኔሆሙ በአምጣነ ይከሉ ፡፡
ከሳቸው ወገን ላንዱም ላንዱ እንደሚቻላቸው መጠን ወነገደ በጊዜሃ ፡፡ ሰጥቷቸው ሄደ ፤
፲፮ ወሖረ ዝኩ ዘኃምስ መክሊተ ነሥአ ወተ ገበረ ቦቱ ፤
፲፮ አምስት መክሊት የተቀበለው ወጥቶ ወርዶ አተረፈ ፤ ወረብኃ ካልዓተ ፭ተ መካልየ ፤ አምስት አተረፈ ዐሥር አደረገ ፡፡
፲፯ ወከማሁ ዘሂ ፪ተ መካልየ ረብኃ ካልዓተ መካልየ ፡፡
፲፯ እንደዚሁ ሁሉ ሁለት መክሊት የተቀበለ ውም ወጥቶ ወርዶ አተረፈ አራት አደረገ ፡፡
፲፰ ወዘአሐደሰ መክሊተ ነሥአ ሖረ ወኃ ለፈ ወከረየ ምድረ ወኃብአ ወርቀ እግዚኡ ፡፡
፲፰ አንድ መክሊት የተቀበለው ግን ሌባ ቢሰ ርቀኝ ወንበዴ ቢቀማኝ ቀጣፊ ቢያታልለኝ ብሎ ፈርቶ ሄዶ ምድር ቆፍሮ የጌታውን ወርቅ ቀበረ ፡፡
፲፱ ወእምድኅረ ብዙኅ መዋዕል አተወ እግዚ እሙ ለእሉ አግብርት ፡፡
፲፱ ከብዙ ዘመን በኋላ የነዚያ የባሮች ጌታቸው መጣ ፤ ወአኀዘ ይትሐሰቦሙ ፤ ተቈጣጠራቸው ፡፡
፳ ወቀርበ ዘኃምስ መካልየ ነሥአ
፳ ወአምጽአ ካልዓተ ኃምሰ መካልየ ፡፡
፳ አምስት መክሊት የተቀበለው ወጥቶ ወርዶ ያተረፈውን አምስቱን ደርቦ አመጣ ፡፡

እንዘ ይብል እግዚኦ ኃምሰ መካልየ ወሀብከኒ ፡፡ አቤቱ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር ፡፡ እንድም ዘወሀብከኒ የሰጠኸኝ አምስት መክሊት ነበር አኮሁ ኃምሰ መካልየ ወሀብከኒ አምስት መክሊት ሰጥተ ኸኝ አልነበረምን ፣ እንድም ዘወሀብከኒ የሰጠኸኝ አምስት አልነበረምን ፡፡
ወናሁ ኃምሰ መካልይ ዘረባሕኩ ዲቤሆን ፡፡
እነሆ ወጥቼ ወርጄ አምስት አትርፌአለሁ ዐሥር አድርጌአለሁ አለው ፡፡

፳፩ ወይቤሎ እግዚኡ አ ገብር ኄር ወምእመን ዘበኅዳጥ ምእመነ ኮንከ ዲበ ብዙኅ እሰይመከ ፡፡

፳፩ አንተ በጐ ባሪያ በጥቂቱ ከታመንክ በብ ዙው እሾምሃለሁ ፡፡
ባእ ውስተ ፍሥሐሁ ለእግዚእከ ፡፡
ጌታህ ተድላ ከሚያደርግበት ግባ ማለት ተሾም ተሸለም አለው ፡፡

፳፪ ወመጽአ ዘ፪ተ መክሊተ ነሥአ ፡፡
፳፪ ሁለት መክሊት የተቀበለውም መጣ ፡፡
ወይቤ እግዚኦ አኮሁ ፪ተ መካልየ ወሀብከኒ ፡፡
አቤቱ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ አልነበረምን ፡፡
ወናሁ ፪ተ ካልዓተ መካልየ ረባሕኩ ፡፡
እነሆ ወጥቼ ወርጄ ሁለት አተረፍኩ አራት አደረግሁ አለው ፡፡

፳፫ ወይቤሎ እግዚኡ አ ገብር ኄር ወምእመን ዘበውኁድ ምእመነ ኮንከ ዲበ ብዙኅ እሠይመከ ባእ ውስተ ፍሥሐሁ ለእግዚእከ ፡፡

፳፫ አንተ በጐ ባሪያ በጥቂቱ ከታመንክ በብዙ ወገን እሾምሃለሁ ጌታህ ተድላ ከሚያደርግበት ግባ ማለት ተሾም ተሸለም አለው ፡፡

፳፬ ወመጽአ በዘ ዘ፩ደ መክሊተ ነሥአ ፡፡
፳፬ አንድ መክሊት የተቀበለውም መጣ ፡፡
ወይቤ እግዚኦ አእምረከ ከመ ብእሲ ድሩክ አንተ ተአርር ዘኢዘራእከ ወታስተጋብእ ዘኢዘረውከ ፡፡
አቤቱ ያልዘራኸውን የምታጭድ ያልበተንኸውን የምትሰበስብ ትነሥእ ዘኢያንበርከ ይላል በሉቃስ ያላኖርኸውን የምታነሣ ጽኑ ጨካኝ መሆንክን አው ቃለሁና ፡፡

፳፭ ወፈሪህየ ሖርኩ ወከረይኩ ምድረ ወደ ፈንኩ መክሊተከ ውስተ ምድር ፡፡
፳፭ ሌባ ቢሰርቀኝ ወምበዴ ቢቀማኝ ቀጣፊ ቢያታልለኝ ብየ ፈርቼ ምድር ቆፍሬ ቀብሬ አኑሬ አለሁ ፡፡ ጠብለልክዋ ውስተ ሰበንየ ይላል በሉቃስ በመጠምጠሚያየ ቋጥሬ ይዣለሁ ፡፡ ናሁ ንሣእ ንዋየከ ፡፡
እነሆ ገንዘብህን ተቀበለኝ አለው ፡፡
፳፮ ወአውሥአ እግዚኡ ፡፡
ጌታው መለሰ ፡፡

ወይቤሎ ኦ እኩይ ገብር ወሀካይ ተአምረኒኑ ከመ ብእሲ ድሩክ አነ አዓርር ዘኢዘራዕኩ ወአስተጋብእ ዘኢዘረውኩ ።

፳፮ ያልዘራሁትን የማጭድ ያልበተንሁትን የምሰበስብ ጽኑ ጨካኝ መሆኔን ታውቃለህን ።

፳፯ ወእምደለወከ ትገብእ ወርቅየ ውስተ ማዕድየ ።

፳፯ ይኸን ካወቅህ ገንዘቤን ልትሰጠኝ የተገባህ ነበር ።
ወመጺእየ አነ ለልየ እምአስተገበርክዎ በርዴ ።
ወጥቶ ወርዶ ለሚያተርፍልኝ በሰጠሁት ነበር ።
አንድም እኔ ወጥቼ ወርጄ ባተረፍኩበት ነበር ።

፳፰ ወይቤሎሙ ለእለ ይቀውሙ ህየ ንሥኡ እምኔሁ ዘንተ መክሊተ ወሀብዎ ለዘቦ ፲ቱ መክሊት ማቴ.፲፫ ፥ ፲፪ ማር.፬ ፥ ፳፭ ሉቃ ፰ ፥ ፲፰ ፲፱ ፥ ፳፮
፳፰ ይህን መክሊት ከሱ ተቀብላችሁ ዐሥር መክሊት ላለው ስጡት ።
፳፱ እስመ ለዘቦ ይሁብዎ ።
፳፱ ላለው ይሰጡታልና ማለት አምስት ላለው አምስት ይሰጡታልና ።
ወይዌስክዎ ።
ይደርቡለታል እለ አንዱን ።
ወለዘሰ አልቦ ዘሂ ቦ የሀይድዎ ።
የሌለውን ግን ያኑ ያለውን ቅሉ ይወስዱበታልና ንሥኡ ፤

፴ ወለገብርሰ እኩይ ወሀካይ አውፅእዎ አፍአ ወደይዎ ውስተ ጽልመት ጸናፊ ኀበ ሀሎ ብካይ ወሐቅየ ስነን ።

፴ ያን ሐኬተኛ ባሪያ ግን ልቅሶ ጥርስ ቍርጥማት ወዳለበት ወደ ጽኑ ጨለማ አግዙት አለ ።
አንድም ቦ ለዘወሀቦ ፭ቱ መክሊተ ብለህ መልስ ።
ባለ ፭ የተባለ ፍጹም ትምህርት ተምሮ መክሮ አስተምሮ ራሱን አስመስሎ ያወጣ ነው ። ባለ ሁለት የተባለ ፍጹም ትምህርት ተምሮ መክሮ አስተምሮ ራሱን አስመስሎ ያወጣ ነው ፥ ቅዱስ ጴጥሮስ ቀሌምንጦስን ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዳወጡ ባሳንድ የተባለ ተምሮ ሳያስተምር የቀረ ነው ።
ወሖረ ዝኩ ዘኃምስ መክሊተ ነሥአ ፥ ፍጹም ትምህርት የተማረው ወጥቶ ወርዶ መክሮ አስተምሮ ራሱን አስመስሎ አወጣ ። ወዘ፩ስ መክሊተ ነሥአ ባለ አንድ ዓሳውያን አሳት ስለት አሳይተው ቢያስከዱኝ መናፍቃን ተከራክረው ምላሽ ቢያሳጡኝ ብሎ ፈርቶ ሃይማኖቱን በልቡ የያዘ ፥ ወይቤሎ አአምረከ ከመ ብእሲ ድሩክ አንተ ። ሕግ ሳትሠራ በአእምሮ ጠባይዕ ዐውቃችሁ መምር ሳትሰጥ በስነ ፍጥረት ተመራምራችሁ በሠራችሁ ብለህ የምትፈርድ ጽኑ ጨካኝ መሆንህን አውቃለሁና አላውያን አሳት ስለት አሳይተው ቢያስከዱኝ መናፍቃን ተከራክረው ምላሽ ቢያሳጡኝ ብየ ፈርቼ ደፈንኩ ውስተ ምድር በልቡናዬ ይዠዋለሁ ። ጠብለልክዋ ውስተ ሰበንየ ባለው በአእምሮዬ ጠብቄአለሁ አለ ገብር ሐካይ ተአምረኒኑ ። ሕግ ሳልሠራ በአእምሮ ጠባይዕ ዐውቃችሁ መምህር ሳልሰጥ በሥነ ፍጥረት ተመራምራችሁ በሠራችሁ ብየ የምፈርድ ጽኑ ጨካኝ መሆኔን ታውቃለህን ፥ ወእምደለወከ አንዲህስ ካወቅህ ሹመትክን ልታበረክተኝ ይገባኝ ነበር ። ለልየ እምአስተገበርክዎ ። ወጥቶ ወርዶ ለሚያስተምር በሰጠሁት ነበር ። አንድም ከሁለት ከሦስት ጀምሮ ባደረስከው እኔ ተራድቸ ባስፋፋሁት ነበር ፥ ንሥኡ እምኔሁ የሱን መምህርነት ነሥታችሁ ለዚያ ደርቡለት ። ወለገብርሰ እኩይ አውፅእዎ ፤ እሱን ግን አውጡት አለ ። ከመንግሥተ ሰማይ አይወጣም በመሀርነት መግባት ቢቀርበት በሕዝባዊነት ይገባል ። ታሪክ ይህም ባባ መልክአ ክርስቶስ ታውቋል ፍጹም ትምህርት ሳያስተምሩ ቀርተዋል በተባሕትዎ ፈጽመውታል በሚሞቱበት ጊዜ መልእክ ገሠጻቸው ቀለሙ አካል እየገዛ ሲወጣ ታይቷል ። አንድም ባሳምስት ሙሴ ነው አምስቱ መጺሕፍት አሉትና ፤ ባለ ሁለት ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ግን ስለሆነ ቅዱስ ጴጥሮስ ይበልጣል ሁለት የተባሉ ብሉይና ሐዲስ ናቸውና ፥ ባሳንድ ይሁዳ አውፅእዎ አሁን የተመቸ ፥ አንድም ባሳምስት ሊቀ ጳጳሳት እንብሮተ እድ ባዕለ ጳጳስ ፤ ሠይመ ቀቢስ ሠይመ ዲያቆን ማጥመቅ ማቍረብ ባለሁለት ቄስ ማጥመቅ ማቍረብ ባሳንድ ዲያቆን ተልእኮ ፥ አንድም ባሳምስት አሚን ፍሥሐ ምሕረት ትዕግሥት ተስፋ ባለሁለት አሚን ፍሥሐ ባሳንድ አሚን አንድም ባሳምስት ጥምቀት ተአምኖ ኃጢአት ከዊነ ሰማዕት ተባሕትዎ ምንኩስና ፤ ባለሁለት ጥምቀት ተአምኖ ኃጢአት ፥ ባሳንድ ጥምቀት ። አንድም ባሳምስት ፍጹም ባለጸጋ ፤ ባስሁለት እንደ መጠኑ ባለጸጋ ፤ ባሳንድ ፍጹም ድኃ ።

በእንተ ኅልቀተ ዓለም ።

፴፩ ወአመ ይመጽእ ወልደ ዕጓለ እመሕያው በስብሐቲሁ ወኵሎሙ መላእክቲሁ ቅዱሳን ምስሌሁ ።

የቀደሙ መምህራን ትመስልን ለምእመናን መክሊትን ለመምህራን ፥ ወአመ ይመጽእን ለባለጸጎች ሰጥተው ይተረጕሙ ነበር ። ዛሬ ሁሉም በሁሉ አሉ ብሎ ትመስልን ለምእመናን ለመምህራን ለባለጸጎች መክሊትን ለምእመናን ለመምህራን ለባለጸጎች ወአመ ይመጽእን ለምእመናን ለመምህራን ለባለጸጎች ሰጥተው ይተረጕማሉ ።

፴፩ ወልደ ዕጓለ እመሕያው መላእክትን አስከትሎ በጌትነት በመጣ ጊዜ ።

እሜሃ ይነብር ዲበ መንበረ ስብሐቲሁ ።
በሚመሰገን ዙፋን ማለት በጌትነት ይገኛል ።

፴፪ ወይትጋብኡ ኵሎሙ አሕዛብ ቅድሜሁ ።

፴፪ ሙታን ሁሉ ከሱ ዘንድ ይሰበሰባሉ ።
ወይፈልጦሙ ዘዘዚአሆሙ ።
እየራስ እየራሳቸው ይለያቸዋል ።
ከመ እንተ ይፈልጥ ኖላዊ አባግዐ እምአጣሊ ።
እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንዲለይ ጻድቃንን ከኃጥአን ይለያቸዋል ።

፴፫ ወያቀውም አባግዐ በየማኑ ።

፴፫ ጻድቃንን በቀኝ ያቆማቸዋል ።
ወአጣሊ በጸጋሙ ።
ኃጥአንንም በግራው ያቆማቸዋል ። ሐተታ ጻድቃንን አባግዕ አላቸው በግ ትሑት ነው ወደ ምድር እያየ ይሄዳል ፡ ጻድቃንም ዕለተ ሞታቸውን እያሰቡ ይኖራሉና ፣ ግብድ ውእቱ ዘይሄሊ ዘእንበለ መቃብሩ ዘውእቱ ርስቱ እንዲል ፣ በግ ሐፍረቷን በላቷ ትሰውራለች ፤ ጻድቃንም የራሳቸውን ኃጢአት በንስሐ የወንድማቸውን ኃጢአት በትዕግሥት ይሰውራሉና ፣ እንድም በግ ጭቃውን አይጸየፈውም ጻድቃንም መከራውን አይሰቀቁትምና ። እንድም በግ ከዋለበት አይታወቅም ፤ ጻድቃንም ካሉበት አይታወቁምና ፣ እንድም ከበግ አውሬ አንዱን የነጠቀለት እንደሆነ ይሸሻል ከሸሸም በኋላ አይመለስም በግ ከበረረ የሰው ልጅ ከተመረረ እንዲሉ ፣ ጻድቃንም ከባልንጀራቸው አንዱ የሞተ እንደሆነ ይመንናሉ ከመነኑም በኋላ አይመለሱምና ፣ እንድም በግ ኑሮው በደጋ ነው ጻድቃንም ኑሯቸው በደጋ መንግሥተ ሰማይ ነውና ፣ በቀኝ ያቆማቸዋል አለ የሚመጣው በክበበ ትስብእት ነውና ፣ እንድም ቀኝ ኃያል ነው ጻድቃንም ለበጎ ሥራ ኃያላን ናቸውና እንድም ቀኝ ፈጣን ነው ፈጣኖች ናቸውና ቅን ነው ቅኖች ናቸውና ፣ እንድም በክብርም ሲል ነው ። ኃጥአንን አጣሊ አላቸው ፍየል ትዕቢተኛ ናት ሽቅብ ሽቅብ ትመለከታለች ። ኃጥእንም ትዕቢተኞች ናቸውና እንድም ፍየል ኃፍረቷን በላቷ አትሰውርም ኃጥእንም የወንድማቸውን ኃጢአት በትዕግሥት የራሳቸውን ኃጢአት በንስሐ አይሰውሩትምና ። እንድም ፍየል ጭቃውን ይጸየፈዋል ። ኃጥእንም መከራውን ይሰቀቁታልና ። እንድም ፍየል ከዋለበት ሁሉ ከእሀል ከተክል እየገባ ሰው ሲያሳዝን ይውላል ፤ ኃጥእንም ሰው ሲያሳዝኑ ይኖራሉና ።
እንድም ፍየል አንዱን አውሬ የነጠቀበት እንደሆነ ለጊዜው ይሸሻል ኋላ ችፍ እያለ ይቀርባል እየነጠቀ ይፈጀዋል ኃጥአንም ከወገናቸው አንድ የሞተ እንደሆነ መነንን ይላሉ ተመልሰው በርስቱ በጉልበቱ በቤቱ በንብረቱ ሲጣሉ ይገኛሉና ፣ እንድም ፍየል ኑሮው ቆላ ነው ኃጥአንም ኑሯቸው ቆላ ገሃነም ነውና ፣ በግራው ያቆማቸዋል አለ የሚመጣ በክበበ ትስብእት ነውና እንድም ፣ ግራ ደካማ ነው ኃጥአንም በጎ ሥራ ለመሥራት ደካሞች ናቸውና ። ግራ ጎዱዕ ነው በጎ ሥራ ከመሥራት ጎዱዓን ናቸውና ። ጠማማ ነው ጠማሞች ናቸውና ፣ በኃሣርም ሲል ነው ፤

፴፬ እሜሃ ይቤሎሙ ንጉሥ ለእለ በየማኑ ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ሰማያት ዘድልው ለክሙ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ።

፴፬ ያን ጊዜ ንጉሥ ክርስቶስ በቀኝ ያሉ ጻድቃንን ቡረከተ ገሪዛን ያደረባችሁ በረከተ ነፍስ ያላችሁ ዓለም ሳይፈጠር በጣዕም በመዓዛ በስን በብርሃን ያዘጋጀላችሁ መንግሥተ ሰማይን ትወርሱ ዘንድ ወደኔ ኑ ይላቸዋል ። ወአስተዳሉኩ እምቅድመ ይኩን ዓለምሙ ለእለ ይነብሩ ውስቴታ እንዲል የሚመጣ በክበበ ትስብእት ነውና ወደኔ ኑ አለ ። እንድም ትእምርተ ፍቅር ነው ።

፴፭ እስመ ርኅብኩ ወአብላእክሙኒ ኢሳ.፶፰ ፥ ፯ ። ሕዝ ፲፰ ፥ ፯-፲፮ ።

፴፭ ብራብ አብልታችሁኛል ።
ጸማዕኩ ወአስተይክሙኒ ።
ብጠማ አጠጥታችሁኛልና ።
ነግደ ኮንኩ ወተወከፍክሙኒ
እንግዳ ብሆን ተቀብላችሁኛልና ።
፴፮ ዓረቄ ወአልበስክሙኒ መክ. ፯ ፥ ፴፮ ።
፴፮ ብታረዝ አልብሳችሁኛልና ።
ደወይኩ ወሐወጽክሙኒ
ብታመም ጠይቃችሁኛልና ።
ተሞቃሕኩ ወመጻእክሙ ኀቤየ ወነበብክሙኒ ።
ብታሰር ወደኔ መጥታችሁ ጠይቃችሁኛልና ።
ሐተታ ፤ ካልጀመሩት አይሆንምና አብላዕክሙኒ አስተይክሙኒ ተወከፍክሙኒ አልበስክሙኒ ሐወጽክሙኒ ነበብክሙኒ አለ የመንግሥተ ሰማይ ዋጋ አይሆንምና አጠገባችሁኝ አኖራችሁኝ አስጌጣችሁኝ አዳናችሁኝ አስፈታችሁኝ አላለም ይህም ሦስቱ የባለጠጎች ሦስቱ የነዳያን ነው ። ርኅብኩ ዓረቄ ተሞቃሕኩ የባለጠጎች ጸማዕኩ ነግደ ኮንኩ ደወይኩ የነዳያን ፤ አልብክኑ ጽዋዓ ማይ ቆሪር ለአስተዮ ጽሙዕ አልብክኑ ጠፈር ለአኅድሮ ነግድ አልብክኑ እግር ለሐውጾ ድውይ እንዲል ። እንድም ለመምህራን በክህደት ምክንያት ብራብ ብጠማ አስተምራችሁኛልና በክህደት እንግዳ ብሆን በትምህርት ተቀብላችሁኛልና በክህደት ምክንያት ልጅነት ባይሰጢኝ በሃይማኖት እንዲሰጢኝ አድርጋችኋልና፤ ባክህደት ብታመም በትምህርት ጠይቃችሁኛልና በማእሰረ ክህደት ብታሰር በትምህርት አስፈትታችሁኛልና ። እንድም ለቀሳውስት

በኃጢአት ከሥጋው ከደሙ ብከለከል በንስሐ ሥጋውን ደሙን ሰጥታችሁኛልና በኃጢአት እንግዳ ብሆን በንስሐ ተቀብላችሁኛልና ልጅነት በኃጢአት ቢነሣኝ በንስሐ እንዲመለስልኝ አድርጋችሁኛልና ። በማእሰረ ኃጢአት ብታሰር በንስሐ አስፈትታችሁኛልና ። አንድም አንድ ወገን ለባሕታውያን ተባሕትዎ ብይዝ በተባሕትዎ መሰላችኛልሁና ።

፴፯ አሜሃ ያወሥኡ ጻድቃን እንዘ ይብሉ እግዚኦ ማዕዜኑ ርኢናከ ርኁበከ ወአብላዕናከ ።

፴፯ ጻድቃንም ሠርተውት ያልሠሩት ይመስላቸዋል
ከትሕትና ወደ ትሕትና ይሄዳሉና
አቤቱ መቼ ተርበህ አይተንህ አብልተንህ ።

፴፰ ወጽሙዓከ ወአስተይናከ ።
፴፰ መቼ ተጠምተህ አይተንህ አጠጥተንህ
ወማዕዜ ርኢናከ እንግዳከ ወተወከፍናከ ።
ምን ጊዜ እንግዳ ሆነህ አይተንህ ተቀብለንህ ።
ወዕሩቀከ ወአልበስናከ ።
ምን ጊዜ ታርዘህ አይተንህ አልብሰንህ ።

፴፱ ወድውየከኒ ወሐወፅናከ ።
፴፱ ምን ጊዜ ታመህ አይተንህ ጠይቀንህ ።
ወሙቁሐከኒ ወመጻእነ ኀቤከ ወነበብናከ ።
መቼ ታስረህ አስፈታንህ ጠየቅንህ ይሉታል ።

፵ ወእምዝ ያወሥአሙ ንጉሥ ወይቤሎሙ አማን እብለክሙ ኵሎ ዘገበርክሙ ለ፩ዱ እምእሉ ንኡሳን አኃውየ እለ የአምኑ ብየ ሊተ ገበርክሙ ።

፵ በኔ ካሙኑ ምእመናን ላንዱ ያደረጋችሁ ለኔ አደረጋችሁልኝ ላንዱ ያደረጋችሁ ለኔ ማድረጋችሁ ነው ብሎ በውነት ይመልስላቸዋል ።

፵፩ ወእምዝ ይብሎሙ ለእለ በፀጋሙ ሑሩ እምኔየ ውስተ እሳት ዘለዓለም ዘድልው ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ ። መዝ. ፮ ፣ ፰ ። ማቴ. ፯ ፣ ፳፫ ። ሉቃ ፣ ፲፫ ፣ ፳፯ ።

፵፩ ከዚህ በኋላ በግራው ያሉ ኃጥአንን መርገመ ጌባል ያደረባችሁ መርገመ ነፍስ ያለባችሁ ለሰይጣን ለሠራዊቱ ወደ ተዘጋጀ ማለት ተፈርዶ ወዳለ ወደማያልፍ ሥቃይ ሂዱ ይላቸዋል ። ሐተታ ፤ የሚመጣ በከበበ ትስብእት ነውና ሑሩ እምኔየ ይላል ። አንድም ትምርተ ፀብ ነው ።

፵፪ እስመ ርኅብኩ ወኢያብላዕክሙኒ ።
፵፪ ብራብ አላበላችሁኝምና ።
ጸማዕኩ ወኢያስተይክሙኒ ፤ ብጠማ አላጠጣችሁኝምና ።

፵፫ ነግደ ኮንኩ ወኢተወከፍክሙኒ ።
፵፫ እንግዳ ብሆን አልተቀበላችሁኝምና ።
ዓረቁ ወኢያልበስክሙኒ ፤ ብታረዝ አላለበሳችሁኝምና ፣ ደወይኩ ወኢሐወፅክሙኒ ፤ ብታመም አልጠየቃችሁኝምና ፤ ተሞቃሕኩ ወኢመጻእክሙ ኀቤየ ወኢነበብክሙኒ ።
ብታሰር መጥታችሁ አልጠየቃችሁኝምና ።

፵፬ አሜሃ ያወሥኡ እሉ በጸጋሙ ፤
፵፬ ያን ጊዜ በግራ ቆመው የነበሩ ኃጥአን ይመልሳሉ ።
እንዘ ይብሉ እግዚኦ ማዕዜ ርኢናከ ርኁበከ ወኢያብላዕናከ ከትዕቢት ወደ ትዕቢት መኄድ ልማዳቸው ነውና ፣ ምን ጊዜ ተርበህ አይተንህ አናበላህ ብለን ። ወማዕዜ ርኢናከ ጽሙዓከ ወኢያስተይናከ ።
ምን ጊዜ ተጠምተህ አይተንህ እናጠጣህ ብለን ።
ወእንግዳከ ወኢተወከፍናከ ፤ ምን ጊዜ እንግዳ ሁነህ አይተንህ አንቀበልህ ብለን ።
ወዕሩቀከ ወኢያልበስናከ ፤ ምን ጊዜ ታርዘህ አይተንህ አናለብስህ ብለን ።
ወድውየከኒ ወኢሐወፅናከ ፤ ምን ጊዜ ታመህ አይተንሀ አንጠይቅህ ብለን ።
ወሙቁሐከኒ ወኢነበብናከ ፤ ምን ጊዜ ታስረህ አይተንህ አንጠይቅህ ብለን ብለው ይመልሱለታል ።

፵፭ ወእምዝ ያወሥአሙ ንጉሥ ወይቤሎሙ አማን እብለክሙ ኵሎ ዘኢገበርክሙ ለ፩ዱ እምእሉ ንኡሳን አኃውየ ሊተ ኢገበርክሙ ።

፵፭ በኔ ካሙኑ ምእመናን ላንዱ አለማድረጋችሁ ለኔ አለማድረጋችሁ ነው ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ብሎ ይመልስላቸዋል ።

፵፮ ወየሐውሩ እሉሂ ውስተ ኵነኔ ዘለዓለም ዮሐ. ፭ ፣ ፳፱ ። ዳን. ፲፪ ፣ ፪ ።
፵፮ ኃጥአን ወደ ማያልፍ ሥቃይ ይሄዳሉ ሲወርዱ ይኖራሉ ። ወጻድቃንሰ ውስተ ሕይወት ዘለዓለም ።
ጻድቃን ግን ወደ ማያልፍ ክብር ይሄዳሉ ። ሲወጡ ሲወጡ ይኖራሉ ። ሐተታ ይህ ሁሉ መነጋገር አለ ቢሉ አዎን ይላሉ ይህማ እንዳይሆን ንቃሕ መዋቲ ባለ ጊዜ ጻድቃን ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርተው ጌታቸውን ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው ይነሣሉ ። ኃጥአንም ከቁራ ሰባት እጅ ጸልመው አሊቃቸውን ዲያብሎስን መስለው ይነሣሉ ጽድቁም ይህ ፍጻሜውም ይህ ነው ። ፍርድ በፊት ወቀሳ ወደኋላ ይሆን የለም ቢሉ የለም ነገሩ የሚያሰኝ ስለሆነ ለሰው በሚረዳ መናገር ነው እንጂ የለም ።

ምዕራፍ ፳፮ ።

፩ ወሶበ ፈጸመ እግዚእ ኢየሱስ ዘንተ ኵሎ ነገረ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ።

፪ ተአምሩ ከመ እምድኅረ ሰኑይ መዋዕል ይከውን ፋሲካ ። ማር ፲፬፣፩ ፣ ሉቃ፣፳፪፣፩ ።

፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አስተምሮ ከፈጸመ በኋላ እስከ ሁለት ቀን ድረስ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁን አላቸው ። ሐተታ የሚያስተምረው ረቡዕ ነው ብሎ እስከ ወደቀበት ሐሙስ ነው ። አንድም ድኅረ ክልኤ ይላል ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ የሚያስተምርበት ማከሰኞ ነው ብሎ ድኅሩ ሐሙስ ነው ፋሲካ ከሐሙስ አይወጣም ። ወይእኁዝዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ፤ ወልደ ዕጓለ እመሕያውን ይይዙታል ማለት እያዛለሁ ወይሰቅልዎ ። እሰቀላለሁ ።

፫ ወእምዝ ተጋብኡ ሊቃነ ካህናት ወሊቃናተ ሕዝብ ውስተ ዓጸደ ሊቀ ካህናት ዘስሙ ቀያፋ ።

፫ ከዚህ በኋላ የሕዝቡ አለቆችና የካህናቱ አለቆች ቀያፋ ከሚባለው ከካህናቱ አለቃ ቦታ ተሰበሰቡ ።

፬ ወተማከሩ ከመ በሀብል የአኃዝዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ወይቅትልዎ ።

፬ በሐሰት አንድ ፡ በሀብል ብለህ አጥብቀህ በድፍረት ይዘው ጌታን ይገሉት ዘንድ መከሩ ።

፭ ወይቤሉ አኮ በበዓል ከመ ኢይትሀወኩ ሕዝብ ።

፭ ነገር ግን ሕዝቡ እንዳይታወኩ በበዓል አይሁን አሉ ።

ዘከመ ረፈቀ ኢየሱስ ለድራር በቢታንያ ወበእንተ ተካይዶቱ ለይሁዳ ።

፮ ወበጺሖ እግዚእ ኢየሱሰ ቢታንያ ቦአ ቤተ ስምዖን ዘለምጽ ። ዮሐ:፲፩፥ ፪ ። ፲፪፥፫ ፤ ማር:፲፬ ፫ ።

፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቢታንያ በደረሰ ጊዜ ከስምዖን ዘለምጽ ቤት ገባ ።

፯ ወመጽአት ኀቤሁ ብእሲት እንተ ባቲ ቢረሌ ዘምሉእ ዕፍረት ዘአልባሰጥሮስ ዘብዙኅ ሤጡ ።

፯ ዋጋው ብዙ የሚሆን የደቀቀ የጣፈጠ ሽቱ ይዛ ፤ አንድም ዘአልባሰ ጢሮስ ይላል በጢሮሳዊ ግምጃ ዋጋ ልክ በሦስት መቶ ወቄት የተገዛ ሽቱ የያዘች ሴት መጣች ።

ወሦጠት ዲበ ርእሱ ለእግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይረፍቅ

ጌታችን ከስምዖን ቤት ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ አፈሰሰችበት ።

፰ ወርእዮሙ አርዳኢሁ አንጐርጐሩ በእንተ ዝንቱ ነገር ።

፰ ደቀ መዛሙርቱ ይህን አይተው አዘኑ ። ወይቤሉ ለምንትኑ ዘመጠነዝ ዕፍረት አኅጐለት ዛቲ ብእሲት፤ይህች ሴት ይህን ያህል ሽቱ ለምን አበላሸች ።

፱ እምኢተሠይጠኑ በብዙኅ ንዋይ ይትወሀብ ለነዳያን ።

፱ ለነዳያን ይመጽወት ዘንድ የሀብዎ ይላል ለነዳያን ይመጸውቱት ዘንድ ለብዙ ዋጋ ባልተሸጠም ነበር አሉ ።

፲ ወአእሚሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ለምንት ታስርኅዋ ለዛቲ ብእሲት ።

፲ ጌታችን እንዲህ ማለታቸውን ዐውቆባቸው ይህችን ሴት ለምን ታዳክሟታላችሁ አላቸው ሠናየ ግብረ ገብረት ላዕሌየ ሊተ ሲል ለኔ በጐ ሥራ ሠርታልኛለችና ።

፲፩ ወለነዳያንሰ ዘልፈ ትረከብዎሙ ።
፲፩ ነዳያንንስ ዘወትር ታገኟቸዋላችሁ ፤
ወጊዜ ፈቀድክሙ ታሤንዩ ሎሙ ።
በወደዳችሁ ጊዜ ታደርጉላቸዋላችሁ ።
ወኪያየሰ አኮ ዘልፈ ዘትረክቡኒ ።
እኔን ግን ዘወትር አታገኙኝም ።

፲፪ ወዘንቲሰ ዕፍረተ ዘሦጠት ዲበ ርእስየ ለቀበርየ ገብረት ።

፲፪ ይህንም ራሴን የቀባችኝ ሽቱ ለምቀበርበት ቀን አስጠብቃዋለች ። ሐተታ ዕለቱን እንዳትቀባው አይሁድ አያስደርሷትም እንደ ሕጋቸው በሦስተኛው እንዳትቀባው ፈጥኖ ይነሣባታልና ፤ ዛሬም እጸድቅበታለሁ ብሎ ከሠራው በኋላ ማዳከም አይገባም አስቀድሞ ግን ቤተ እግዚአብሔር ልነጽበትን ለነዳያን ልሰጣቸውን ብሎ ያማከረ እንደሆነ ሕንጸ እግዚአብሔር ሰው በረኃብ ሲፈርስ ሲበሰብስ ለነዳያን ስጥ እንጂ ማለት ይገባል ከሠራ በኋላ ግን እንዲህ ማለት አይገባም ያኑ ከሙተው ያደርሰዋልና ፤ ታሪክ አባ ኢዮብ አባ ጴሜን የሚባሉ ፍጹማን መነኩሳት ነበሩ ገባረ ሪፍ የሚባል በዓለም የሚኖር ደግ ሰው ነበረ እየመጣ ይጠይቃቸዋል ሊጠይቃቸው መጥቶ ሳለ አባ ጴሜን እንደምን ሁነህ ትኖራለህ አለው ተክል ተክየ ራሴን ረድቼ እንግዳ ተቀብዬ ቢቻለኝ ለነዳያን ተርፌ እኖራለሁ አለው መልካም ይዘሃል ብሎ አሰናበተው ከዚህ በኋላ አባ ኢዮብ መጣ ገባረ ሪፍ መጥቶ ነበር አለው ምን ብለህ አሰናበትከው አለው እንዲህ ቢለኝ መልካም ይዘሃል አልሁት አለው ።መልካም አላደረግህ ምእኛን መስለህ ኑር እንዳትለው አለው አጥፍቻለሁ ጠርቼ ላመጣው ብሎ ጠርቶ አመጣው እኛን መስለህ ኑር አለው ከነሁሉም አይቻለኝም ብሏል አባ ኢዮብ አላበጀሁም ማረኝ ብሏል ። ይህች ሴት ከራስ ጸጕሯ እስከ እግር ጽፍሯ ይህ ቀራት የማትባል መልክ መልካም ናት መላ አካሏን የሚያሳይ መስታወት አሳት ልብሷን አኑራ መልኳን አይታ መፍረስ መበስበስ ሳይቀር እንዲህ ማማር ምን ይረባል የዚያስ የዚያስ ኃጢአት የሚያስተሰርይ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቷል አሉ ለሱ የምቀባው ሽቱ ገዝቼ እሄዳለሁ ብላ በዝሙቷ

የሰበሰበችው ሦስት መቶ ወቄት ወርቅ አላት ይዛ ሄደች ።
ዲያብሎስ ታመልጠኛለች ይህን ጊዜ ላስታት ብሎ ቀድሞ ከምታውቀው አንዱን መስሎ በአምሳለ ወሬዛ ሠናየ ላህይ ከመንገድ ቆየት ወዴት ትሄጃለሽ አላት ዝም አለችው አንች ባትነግሪኝ እኔ እነግርሽ የለም እንግዳ ወንድ መጥቶብሽ ለሱ ልትቀቢው ሽቱ ልትገዢ ትሄጃለሽ አላት አዎን አለችው ። ይህም አይደለም ፍቅሩ ያላለቀለት ወንድ መጥቶብሽ ለዚያ የምትቀቢው ሽቱ ልትገዥ ትሄጃለሽ አላት አዎን አለችው ይህም አይደለም በጥቂት ገንዘብ ብዙ ገንዘብ የሚሸጥ ነጋዴ መጥቶብሽ ለሱ የምትቀቢው ሽቱ ልትገዥ ትሄጃለሽ አላት አዎን አለችው ሁሉንም አዎን አዎን ትያለሽ ማናቸው ነው አላት እንግዳ ወንድ መጥቶብሽ አልከኝ ከዚህ ዓለም ልዩ የሚሆን ጌታ መጥቷል ፍቅር ያላለቀለት ወንድ መጥቶብሻል ላልከኝ ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት እንዲል ። የሰው ፍቅር አገብሮት ሊሞት መጥቷል በጥቂት ገንዘብ ብዙ ገንዘብ የሚሸጥ ባለጸጋ ነጋዴ መጥቶብሻል ላልከኝ አዎን በጥቂት ትሩፋት ብዙ ክብር የሚሰጥ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቷልና ለሱ የምቀባው ሽቱ ልገዛ እሄዳለሁ ብላ ስሙን ብትጸራበት እንደ ትቢያ በኖ እንደ ጢስ ተኖ ጠፍቶላታል ። ከዚህ በኋላ ሃድኖክ የሚባል ባለጸጋ ነጋዴ አለ ሄዳ ለነገሥታት የሚገባ ሽቱ አምጣ ብላ ሦስት መቶ ወርቅ ሰጠችው በሀገራቸው ሐሰት የለምና ይህን ያህልስ የሚያወጣ የለኝም አላት ኢሉ የማያውቀው እናቱ የምታውቀው ዳዊት ሰሎሞን ተቀብተውለት የተረፈ ነበር ከእንዲህ ያለ ቦታ አለ ሽጥላት ብላው ሽጦላት አምጥታ ቀብታዋለች ። ይህ ብቻም አይደለ ጌታ ግብጽ ሲወርድ ሰሎሜም ፊያታይ ዘየማን ይዘውት ሳለ ክልብሱ ላይ ወዛ ቢያጥቡት ሰፈፈ ይህን በዕቃ አኑረውታል ይህም ተጨምሮበታል ።

፲፫ አማን እብለክሙ በኀበ ሰበክዋ ለዛቲ ወንጌል ይንግሩ ውስተ ኵሉ ዓለም ዘገብረት ዛቲ ብእሲት ተዝካረ ላቲ ወይዝክርዋ ።

፲፫ ወንጌል በተነገረችበት ቦታ ሁሉ ይህች ሴት የሠራችውን ሊነግሩላት ይገባል ብዬ እንዲገባ በውነት እነግራችኋለሁ ። ይህንም ይዘው አራቱ ሁሉ ጽፈዋታል ።

፲፬ ወእምዝ ሖረ ፩ዱ እም፲ቱ ወ፪ቱ አርዳኢሁ ዘስሙ ይሁዳ አስቆሮታዊ ኀበ ሊቃነ ካህናት ።
ማር፡፲፬ ፣ ፲ ሉቃ፡ ፳፪ ፣ ፫ ።

፲፬ ከዚህ በኋላ ከሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ አንዱ የአስቆሮት ሰው የሚሆን ይሁዳ ወደ ሊቃነ ካህናት ሄደ ። ሐተታ እንዲያው አይደለም በደብረ ዘይት ሲበሉ አማን እብለክሙ ከመ ፩ዱ እምኔክሙ ያገብአኒ አላቸው ። ወአነኑ እንጋ እግዚኦ አነኑ እንጋ ። የማሲዝህ እኔ ነኝ እኔ ነኝ ይባባሉ ጀመሩ ታሪክ በደብረ ዘይት ከነበሩ እእባን አንዱን መጥተህ መስክርበት አለው መጥቶ በይሁዳ ራስ ላይ ሦስት ጊዜ ዞሮ ንጹሕ ደም የምታስፈስስ ይሁዳ ወዮልህ ብሎ መስክሮበታል ዛሬስ አለ እስና ይህ መሠርይ ደንጊያ ያናግርብኝ ጀመር እንኪያስ በማኝ ያግኘኝ ብሎ ወጥቶ ሄዷል ።

፲፭ ወይቤሎሙ ሚመጠነ ትሁቡኒ እመ አገብአ ለክሙ ።

፲፭ ባሲዛችሁ ምን ያህል ትሰጡኛላችሁ አላቸው ።
ወተናገርዎ ምስሌሁ ወተሰነአው ከመ የሀብዎ ፴ ብሩረ ።
ሠላሳ ብር እንሰጥሃለን አሉት ። ወአስተሐለቁ ነገረ ይላል በሉቃስ ነገር ቆረጹ ነገር አቆሙ ነገር ወሰኑ ።

፲፮ ወእምይእቲ ዕለት አኀዘ ይኅሥሥ ሳሕተ ከመ ያግብአ ሎሙ ።

፲፮ ከዚያ ቀን ጀምሮ ከዚያ ቀን ወዲህ ሊያሲዘው ምግላል ቦታ ይሻ ነበር ።

በእንተ ደኃሪት ድራር ።

፲፯ ወበቀዳሚት ዕለተ ፍሥሕ መጽኡ አርዳኢሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ወይቤልዎ በአይቴ ትፈቅድ ናስተዳሉ ለከ ትብላዕ ፍሥሐ ። ማር፡ ፲፬ ፣ ፳፪ ሉቃ፡ ፳ ፣ ፯-፯ ።

፲፯ ፋሲካ ከሚውልባቸው ከ፯ቱ ዕለታት በመጀመሪያዪቱ ቀን ፣ አንድም ወአመ ቀዳሚት ዕለተ ፍሥሕ ይላል በመጀመሪያዪቱ ፋሲካ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ጌታ ቀርበው በጉን ትበላ ዘንድ በወዴት ልና ዘጋጅልህ ትወዳለህ አሉት ፣ ሑሩ ወአስተዳልዉ ዘንበልዕ ፍሥሐ ብሏቸዋል በሉቃስ ።

፲፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ሑሩ ውስተ ሀገር ኀበ እገሌ ።

፲፰ ጌታም ወደእገሌ ሀገር ሂዱ አላቸው ። እንደ ማርቆስ ምልክት ነገሮ ይሰዳቸዋል ። ወበልዎ ይቤለከ ሊቅ ጊዜየ በጽሐ በኀቤከ እገብር ፋሲካ ምስለ አርዳእየ።መምህር ከደቀ መዛሙርቴ ጋራ ባንተ ዘንድ በዓል የማከብርበት ቀን ደርሷል አለህ በሉት አላቸው ።

፲፱ ወገብሩ አርዳኢሁ በከመ አዘዞሙ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፱ ደቀ መዛሙርቱ ጌታ እንዳዘዛቸው አደረጉ። አስተዳለው ሎቱ ፍሥሐ ።
በጉን የሚያርዱበት ወቅለምት ደሙን የሚቀበሉበት ብርት ሥጋውን የሚቀቅሉበት ድስት አዘጋጅተዋል ።

ዘከመ ከሥተ ሎሙ ለዘያገብእ ።

፳ ወምሴተ ከዊኖ ረፈቀ ምስለ ፲ቱ ወ፪ቱ አርዳኢሁ ። ማር.፲፬፡፲፯ ሉቃ.፳፪፡፲፬ ሉቃ.፲፫፡፳፩ ።

፳ ሲመሽ በመሽ ጊዜ ከሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋራ ተቀመጠ ።

፳፩ ወእንዘ ይበልዑ ይቤሎሙ አማን እብለክሙ ከመ ፩ዱ እምኔክሙ ያገብአኒ ።

፳፩ ሲበሉ ከናንተ አንዱ ያሲዘኛል ብሎ እንዲያሲዘኝ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ።

፳፪ ወተከዙ ጥቀ ።

፳፪ ፈጽመው አዘኑ ።

ወአኃዙ ይበልዎ በበ፩ዱ እኑኑ አንጋ እግዚኦ ። እያንዳንዳቸው አቤቱ የሚያሲዝህ እኔ ነኝ እኔ ነኝ ይባባሉ ጀመር ።

፳፫ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ዘያወርድ እዴሁ ምስሌየ ውስተ መጸብሕየ ውእቱ ያገብአኒ ።

፳፫ ከኔ ጋራ ወጥ የሚያወጣው እሱ ያሲዘኛል አላቸው ። ሐተታ ለልማዱ ጌታ ስድስቱን አቁሞ ስድስቱን አስቀምጦ ይዞ ይበላሉ ይመገባሉ ። ዛሬ የተቀመጡ ነገ ይቆማሉ ወጥ የሚያወጣው በተራ ነው ጌታ እያወጣ ይበላል አውጡልኝ አይልም ስድስተኛው ላምስቱ ለራሱም እያወጣ ይበላል በዚያ ቀን ከተቀመጡት አንዱ ይሁዳ ነበር ወጥ ማውጣትም ተራው የይሁዳ ነበርና እንዲህ አለ ።

፳፬ ወልደ ዕጓለ እመሕያውሰ የሐውር በከመ ተሠርዓ በእንቲአሁ ። መዝ.፺፡፲ ።

፳፬ ተጽሕፈ ሲል ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስም ስለሱ እንደተጻፈ ይሄዳል ማለት ይሞታል ወባሕቱ አሌ ሎቱ ለውእቱ ብእሲ ዘያገብአ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

ነገር ግን ምክንያት ሁኖ ለሚያሲዘው ለዚያ ሰው ወዮለት እምኃየሰ ሶበ ኢተወልደ ለውእቱ ብእሲ ። ባልተወለደ በተሻለው ነበር ፤ ሐተታ ። እናቱን ይዳፋት ማለት ነው ቢሉ ኢተፈጥረ ሲል ነው ባልተፈጠረ በተሻለው ነበር አሪት ዘልደት እንዲል ዘፍጥረት ሲል ። ይህስ ፍጠረኝ ብሎ ፈጥሮታልን ቢሉ ቢፈጥረውስ ግዕዛኑን ነሥቶ ፈጥሮታልን ።

፳፭ ወአውሥአ ይሁዳ ዘያገብአ ወይቤ አኑኑ አንጋ ውእቱ ረቢ ።

፳፭ የሚያሲዘው ይሁዳም የሚያሲዝህ እኔ ነኝ አለው ተለይቼ ብቀር ይታወቅብኛል ብሎ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አንተ ትቤ ።

አንተ ትላለህ አለው ። መስወር. እንድም በፈቃዱ የምሞተውን ሞት በግድ አስገድለዋለሁ ትላለህ ። ታሪክ ጌታ ሙሴን በግብጻውያን ሞተ በኵር አምጥቼ አወጣችኋለሁ አለው እንዲህማ ከሆነ የእሥራኤልስ በኵር ሊሞት አይደለምን አለው ፤ እንዲህስ እንዳይሆን የሚያዝያ ጨረቃ ሠርቅ ባደረገች ባሥር ቀን ቀንዱ ያልከረከረ ጥፍሩ ያልዘረዘረ ጠጉሩ ያላረረ ዓመት የሆነው ጠቦት ያለው ከመንጋው ። የሌለው ገዝታችሁ እስከ ፲፬ ቀን አስሩችሁ ባ፲፬ኛው ቀን ፩ዱን ሰዓት ከ፲ ክፍላችሁ ፩ዱን እጅ ትታችሁ በ፱ እጅ ብርሃን ከሌሊቱም ፩ዱን ሰዓት ከ፲ ክፍላችሁ ባንዱ እጅ ጨለማ ሠውት።ስትሠውትም ፯ ዐሥር ፲፪ ሁናችሁ ። ያለው ቤተሰቡን ይዞ የሌለው ጐረቤቱን ጠርቶ አንድ በግ እንድትጨርሱ ሁናችሁ ደሙን መቃን መድረኩን እርጩት ያን እያየ ሞት በኵር ይከለክልላችኋል ፡ ዝግኑን ቅቅሉን ብርንዶውን አትብሉ ጥብሱን ብሉ ኢታትርፉ እስከ ደግደግ እንዲል ። አትርፋችሁ አታሳድሩ ካንዱ ወዳንዱ አትውሰዱት የበላችሁትን በሌታችሁ የተረፋችሁን ከእሳት ጨምሩት ሐምለ ብኒእ ረብርቡበት ብሎታል በሀገራቸው አራት ነገር ያመጣል የወይን ቅጥራን የበለስ ቅጥራን የሥንዴ ቅጥራን አዞ ከል ። በዚያ ወራት የሚበሉት ቂጣ ነውና እንዳረቄ እንዲበትንላቸው ። ስትበሉትም ጫማችሁን አዝባችሁ ዝናራችሁን ታጥቃችሁ ኩፌታችሁን ደፍታችሁ በሎታችሁን ይዛችሁ እየቸኮላችሁ ብሉት አጥንቱን አትስበሩት ብሏቸዋል ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው ። በግዕ የጌታ ምሳሌ ዓመት የሆነው ጠቦት ወርድ እንጂ ቁመት አያክልም ። ጌታም ፍጹም የሠላሳ ዓመት ጐልማሳ ቢሆን ነውና የተሰቀለ ዓመት የሆነው ጠቦት ቀንዱ ያልከረከረ ጥፍሩ ያልዘረዘረ ጠጉሩ ያላረረ ማለቱ ምክንያተ ኃጢአት የለበትምና ። የሚያዝያ ጨረቃ ሠርቅ ባደረገች ባሥር ቀን ዋጅታችሁ እስከ ዐሥራ አራት አስሩችሁ ባሥራ አራት ቀን ሠውት ማለቱ የጌታም ምክረ ሞቱ ባሥር ተጀምሮ ባሥራ አራተኛው ቀን ተፈጽሟል ። በሁለት እጅ ብርሃን ባንድ እጅ ጨለማ ሠው ማለቱ ከነግህ እስከ ቀትር ብርሃን ሁኑዋል ። ከቀትር እስከ ሰዓት ጨለማ ሁኑዋል ። ወጸልመ ኵሉ ዓለም እንዲል ። በሠርክ ብርሃን ሁኑዋል ። ወፍና ሠርክ ይበርህ እንዲል ፤ ስትሠዉትም ሰባት ዐሥር አሥራ ሁለት ሁናችሁ ሠዉት ማለቱ ሰባት በሳቸው ፍጹም ነው ዐሥርም በኛ ፍጹም ነው ፍጹማን ሁናችሁ ተቀበሉ ሲል ፲፪ ማለቱ ለጊዜው የሚቀበሉት ዐሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ናቸው ፍጻሜው ግን ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ናቸውና ፤ ደሙን መቃን መድረኩን እርጩት ማለቱ ለጊዜው ያን እያየ ቸነፈር ይከለክልላቸዋል ። ዛሬም ሥጋውን ደሙን ከሚቀበሉ ምእመናን አጋንንት ላለመቅረባቸው ምሳሌ ። ዝግኑን ቅቅሉን አትብሉ ማለት ሙስና መቃብር አገኘው አትበሉ ሲል ነው ። ብርንዶውን አትብሉ ማለቱ ደም ካለ ነፍስ አትለይም ። እስመ ነፍስ ተኃድር በደም እንዲል ነፍስ ያልተለየውን ሥጋውን እንበላለን አትበሉ ሲል ጥብሱን ብሉ ማለቱ መለኮት

የተዋሐደውን ነፍስ የተለየችውን ሥጋውን እንበላለን በሉ ሲል ነው አታሳድሩ እለ ካሣ ሳይፈጸም አላደረምና ካንዱ ወደ እንዱ አትውሰዱት እለ ለጊዜው መካነ መስቀሉ ለመካነ መቃብሩ ቅርብ ነው ፍጻሜው ግን ዛሬም መሥዋዕት ካንዱ ሠርቶ ወዳንዱ ወስዶ መሠዋት አይገባምና የበላችሁትን በልታችሁ የተረፋችሁን ከእሳት ጨምሩት ማለቱ የተቻላችሁን ያህል ምሥጢር መርምራችሁ የቀረውን መንፈስ ቅዱስ ያውቃል በሉ አትጋፉ ሲል ነው ። እሳት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ፤ ሐምለ ብኂእ ረብርቡብት ማለቱ ለጊዜው ቢዚያ ወራት የሚበሉት ቂጣ ነበርና እንደ አረቂ አንዲበትንላቸው ነው ዛሬም ሥጋውን ደሙን መቀበል የሚገባ የበሉት የጠጡት ከሆድ ሲጠፋ ላፍ ምሬት ሲሰማ ነውና ፤ ጫማችሁን አዝባችሁ እለ ምግባረ ወንጌልን ሠርታችሁ ዝናራችሁን ታጥቃችሁ እለ ንጽሕና ይዛችሁ ኩፌታችሁን ደፍታችሁ እለ አክሊለ ሦከን እያሰባችሁ በሎታችሁን ይዛችሁ እለ ነገረ መስቀሉን እያሰባችሁ ሲል ነው እየቸኮላችሁ ብሉት ማለቱ ለጊዜው መንገደኞች ናቸው ፍጻሜው ግን ሞት እሰብን እያላችሁ ኑሩ ሲል ነው ። እረጋዊ መንፈሳዊ ፤ ድርሳን ፤ ዓብድ ውእቱ ዘይሄሊ ዘእንበለ መቃብሩ ዘውእቱ ርስቱ እንዲል አጥንቱን አትሰበሩት ማለቱ ለጊዜው ግብጻውያን ሲጎዱ እሥራኤል አለመጐዳታቸውን መናገር ነው ፤ ፍጻሜው ግን ኃጥአን ሲጐዱ ጻድቃን ላለመጐዳታቸው ምሳሌ ነው በቁሙም የሁለቱን ወንበዶች ጭንና ጭናቸውን እየሰበሩ ሲያወርዷቸው የሱን አልሰበሩትምና ፀፅሞ ኢትሰብሩ እንዲል ፤ እንደ አርዮስ ፍጡር በመለኮቱ አትበሉ ሲል ነው ከዚህም አሪትን ሠርቶ አሳልፏታል ፤ ንጉሥ ቀድሞ ሹሞት የነበረውንና ኋላ የሚሾመውን አቅርቦ ያን ወቅሶ ሽሮ ይህን እንዲሾም እሱም ወንጌልን የሚሠራ ነውና ።

ዘከመ ሠርዓ ኢየሱስ እኰቴተ ቍርባን ።

፳፮ ወእንዘ ይበልዑ ነሥአ ኅብስተ እግዚእ ኢየሱስ ባረከ ። ፩፥ ቆሮ ፲፩ ፥ ፳፫ ።

፳፮ ሲበሉ ጌታ ዳቦውን አንሥቶ ይዞ ባረከ አከበረ ለወጠ ።

ወፈተተ ። ገመሰ ቆረሰ ። እንድም ባረከ ገመሰ ቆረሰ ፈተተ አጠቃቀነ ዐሥራ ሦስት አደረገ ፤ ጌዴዎን ዓሥራ ሦስት ሁኖ ሠውቷልና እንድም ባሥራ ሦስቱ ዕፀወ ዕጣን ምሳሌ እንድም ዐሥራ ሦስቱን ጸዋትወ መከራ እቀበልላችኋለሁ ሲል አክሊለ ሦከ ተኰርዖ ርእሰ ተጸፍዖ መልታሕት ተወክፎ ምራቅ ሰትየ ሐሞት ተእስሮ ድኅሪት ተቀስፎ ዘባን ርግዘተ ገቦ ርግዘተ ገቦ ከሞተ በኋላ ነው አይስማውም ብሎ ጸዊረ መስቀል ኃምስቱ ቅንዋት እግሩን እየራሱ ቸንከረውታል ያሉ እንደሆን የተመቸ ነው ። ደርበው ቸንከረውታል ያሉ እንደሆን ብሱን ያያል ። አንዱን እሱ ተቀብሎታል ፲፪ን ለሐዋርያት ሰጥቷቸዋል ዝ ሥጋየ ዝ ደምየ ብሏቸዋልና ለማስደፈር ጥዒሞ አጥዓሞሙ እንዲል ። እንድም ሳይቀበል አቀብሏቸው ቢሆን ቄሱ አቀብሏቸው ሳይቀበል በወጣ ነበርና ተቀብሎ ያቀብል ለማለት አብነት ለመሆን ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ። ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ ። ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚሠዋው ሥጋየ ይህ ነው ብሉ ።

፳፯ ወነሥአ ጽዋዓኒ ወአእኰተ ።

፳፯ ጽዋውንም ይዞ አክብሮ ለውጦ ትኩስ ደም አድርጎ ።

፳፰ ወወሀቦሙ እንዘ ይብል ስትዩ እምኔሁ ኵልክሙ ዝ ውእቱ ደምየ ዘሐዲስ ሥርዓት ዘይትከዓው በእንተ ብዙኃን ለኀድገተ ኃጢአት ።

፳፰ እንግዳ ሥርዓት የሚሆን የሐዲስ ርስት የመንግሥተ ሰማያት መጽኛ የሚሆን በተሐድሶ ጸንቶ የሚኖር ስለ ብዙ ሰዎች የሚፈስ ደሜ ይህ ነው ከሱ ጠጡ ብሎ ሰጣቸው ሐተታ፤ በከፊል ተናገረው አንድ ሰው ተቀብሎ አይፈጽመውምና እስከ ዕለተ ምጽአት ሲሰጥ ይኖራልና ለኀድገተ ኃጢአት ኃጢአት ሊሰረይ ።

፳፱ ወናሁ እብለክሙ ኢይሰቲ እንከ እምይእዜ እምዝንቱ ሐጺረ ፍሬ ወይን እስከ እንታክቲ ዕለት አመ እሰትዮ ሐዲሰ ምስሌክሙ በመንግሥተ አቡየ ።

፳፱ ባባቴ መንግሥት ማለት ባባቴ ሥልጣን ታድሼ ተነሥቼ ከናንተ ጋራ በጥብርያዶስ አስከም መጣበት ቀን ድረስ ከዚህ የወይን ፍሬ ጭማቂ አል ጠጣም ብየ እነግራችኋለሁ ።

፴ እንቢቦሙ ማር. ፲፬ ፤ ፳፮ ዮሐ. ፲፯ ፤ ፴፱ ዘካር. ፲፫ ፤ ፯ ።

፴ በአራት የሚደገም አለ ያን ደግመው ። ሰቢሆሙ ። ሥጋውን ደሙን ተቀብለው እንድም እንቢቦሙ አቡነ ዘበሰማያት ደግመው ወሰቢሆሙ ነገረ ጳራቅሊጦስን ተጫውተው ።

፴፩ ወፅኡ ውስተ ደብረ ዘይት ።

፴፩ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ ። ሐተታ ሥጋውን ደሙን በመብል በመጠጥ ያደረገውን በሌላ ያላደረገው ስለምን ቢሉ የቀረው ከብት በአፍአ ይቀራል መብል መጠጥ ከሰውነት ይዋሐዳልና በውነት እንደ ተዋሐደን ለማጠየቅ ። እንድም መብል መጠጥ ያፋቅራል እንዳፋቀረን ለማጠየቅ ያውስ ቢሆን በሥንዴ በወይን ያደረገው በሌላ ያላደረገው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ትንቢት እምፍሬ

ሥርናይ ወወይን ወቅብዕ በዝኃ ። ቀዳሚ ሕይወቱ ለሰብእ እክል ወማይ ወይን ወሥርናይ ለዘኢይሰቲ ወይኑ ምንትኑ ሕይወቱ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም መልከ ጼዴቅ በሥንዴ በወይን ይሠዋ ነበር ትንቢቱን ዐውቆ እናግሯል ምሳሌውንም እንጂ ባወቀ አስመስሏል ምሥጢሩ ምንድነው ቢሉ ጌታችን እመቤታችን ቢበሉ የኖሩ ሥንዴ ወይን ነበረ ፍጹም ሥጋውን ፍጹም ደሙን እንደ ሰጠን ለማጠየቅ ። እንድም በመስለ ነገር ለመስጠት ሥንዴ ሥብ ሥጋ ይመስላል ወይንም ትኩስ ደም ይመስላልና ። አንድም ሥንዴ ልባም ሴት የያዘችው እንደሆነ ነውር የለበትም ነውር የሌለበት ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል ወይንም አንድ ጊዜ የጣሉት እንደሆነ ኃይል እየጨመረ ይሄዳል ኃይል የምትሆን ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል ።

ወእምዝ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኵልክሙ ትክህዱኒ በዛቲ ሌሊት ከዚህ በኋላ ጌታ በዚች ሌሊት ሁላችሁ ትክዱኛላችሁ አላቸው ።

እስመ ይብል መጽሐፍ እቀትል ለኖላዊ ወይዘረዉ አባግዕ መርዔቱ ።

መጽሐፍ ጠባቂ ክርስቶስ ይሞታል የመንጋው በጎች ሐዋርያት ይበተናሉ ብሏልና ።

፴፪ ወእምድኅረ ተንሣእኩ እቀድመክሙ ገሊላ

፴፪ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ ማለት ከተነሣሁም በኋላ መታየትን በገሊላ እጀምርላችኋለሁ ።

፴፫ ወአውሥአ ጴጥሮስ ።

፴፫ ጴጥሮስም መለሰ ።

ወይቤሎ ለእመኒ ኵሎሙ ክህዱከ አንስ ኢይክህደከ ግሙራ ።

ሁሉም ቢክዱህ እኔ አልክድህም አለው ።

፴፬ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አማን እብለከ ከመ በዛቲ ሌሊት ሥልስ ትክህደኒ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ማር ፲፬ ፡ ፴ ።

፴፬ ጌታም በዚች ሌሊት ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ብየ እንድትክደኝ በውነት እነግርሃለሁ አለው ።

፴፭ ወይቤሎ ጴጥሮስ እመውትኒ ምስሌከ ወኢይክህደከ ዮሐ ፲፫፡፴፯ ማር ፲፬፡፴፩ ሉቃ ፳፪፡፴፫

፴፭ ጴጥሮስም ካንተ ጋራ እሞታለሁ ሞትከን ሞት እደርጋለሁ እንጅ አልክድህም አለው ፤

ወከማሁ ይቤሉ ኵሎሙ አርዳኢሁ ።

ተመክቶ ያስመከቸዋል ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ እንደሱ ከሱ ጋራ ሞትከን ሞት እናደርጋለን አንክድህም አሉ።

ዘከመ ጸለየ ኢየሱስ በጌቴሴማን ።

፴፮ ወእምዝ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ ምስሌሆሙ ውስተ ዓጸደ ወይን ዘስሙ ጌቴሴማን ።

፴፮ ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ጌቴሴማን ከሚባለው ወይን ቦታ ሄደ ።

ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ንበሩ ዝየ እስከ ሶበ አሐውር ከሀ ወእጼሊ ።

ደቀ መዛሙርቱን ከዚያ ሂጀ እስከጸልይ ድረስ ከዚህ ቆዩ አላቸው ። አንድም እጼሊ ይላል እጸልይ ዘንድ ።

፴፯ ወነሥአሙ ምስሌሁ ለጴጥሮስ ወለ፪ሆሙ ደቂቀ ዘብዴዎስ ።

፴፯ ሦስቱን ባለሟሎቹን አስከትሎ ሂዶ ስምንቱን በጌቴሴማኒ ትቶ ፤

ወአኀዘ ይተክዝ ወይኀዝን ።

ያዝን ይቆረቆር ጀመር ።

፴፰ ወእምዝ ይቤሎሙ ተከዘት ነፍስየ እስከ ለሞት ።

፴፰ ከዚህ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ነፍሴ እስከ መለየት ደርሳ አዘነች አላቸው ።

ወንበሩ ዝየ ።

ክዚህ ቆዩ ።

ወትግሁ ምስሌየ ።

ከኔ ጋራ ለመኖር እንደኔ ተግታችሁ አመልክቱ ።

፴፱ ወተአተተ ሕቀ እምሀየ ወሰገደ በገጹ ።

፴፱ ከዚያ ጥቂት እልፍ ብሎ ግንባሩን ምድር እስነክቶ ሰገደ ።

በሉቃስ መጠነ ሙጋረ እብን ይላል ድንጊያ ወርውሮ እስከሚደርስበት ።

ወጸለየ ።

አመለከተ ።

ወይቤ አ አቡየ እመሰ ይትከሃል ይኅልፍ እምኔየ ዝንቱ ጽዋዕ ።

ያለኔ ሞት የዓለሙ ድኅነት ያለኔ ሕማር የዓለሙ ክብር አይቻልም እንጂ የሚቻልስ ከሆነ ይህ ጽዋዕ ሞት ይለፍልኝ ወባሕቱ ፈቀደ ዚአከ ይኩን ወእኮ ፈቀደ ዚአየ ። ነገር ግን ያንተ ፈቃድ ይደረግ እላለሁ እንጂ የኔ ፈቃድ ይደረግ አልልም ። አንድም በኔ ሞት የዓለም ድኅነት በኔ ኃማር የዓለምም ክብር የሚቻልስ ከሆነ እኔ ከሞትሁላቸው ከኔ ሞት የተነሣ ይህ ጽዋዕ ሞት ይቅርላቸው ። አንድም ከኔ ለምእመናን ይለፍላቸው ፤ እኔን አብነት አድርገው ይሙቱ ።

ወባሕቱ ፈቀደ ዚአከ ይኩን ወእኮ ፈቃደ ዚአየ ።

ነገር ግን የኔ ፈቃድ ካንተ ፈቃድ ልዩ ሁኖ የኔ ፈቃድ ይሁን አልልም የኔ ፈቃድ ካንተ ፈቃድ ጋራ አንድ ነውና ያንተ ፈቃድ ይሁን እላለሁ እንጂ ፤

፵ ወሖረ ኀበ አርዳኢሁ ።

፵ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሄደ ።

ወረከቦሙ እንዘ ይነውሙ ።

ተኝተው አገኛቸው ።

ወይቤሎ ለጴጥሮስ ከመዝኑ ስእንከሙ ተጊሃ አሐተ ሰዓተ ምስሌየ ።
ጴጥሮስን ከኔ ጋራ ለመኖር እንደኔ አንድ ሰዓት መትጋት ተሳናችሁ አለው ።

፵፩ ትግሁ ወጸልዩ ከመ ኢትባኡ ውስተ መንሱት ።

፵፩ ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት ወደ መከራ ወደ ገሃነም እንዳትገቡ ተግታችሁ ለምኑ ።
እስመ መንፈስ ይፈቅድ ።
ነፍስ ሥራ ልትሠራ ትወዳለችና ትግሁ ።
ወሥጋ ይደክም ።
ሥጋ ግን ደካማ ነውና ኢትባኡ ላለው ።

፵፪ ወካዕበ ሖረ ወጸለየ ።
፵፪ ሁለተኛ ሄዶ አመለከተ ፤
ወይቤ እመ ይትከሃል ይኅልፍ እምኔየ ዝንቱ ጽዋዕ እንበለ እስተዮ ይኩን ፈቃድከ እንዳለፈው በል ።

፵፫ ወገብአ ካዕበ ኀበ አርዳኢሁ ።
፵፫ ፪ተኛ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሄደ ፤
ወረከቦሙ እንዘ ይነውሙ ።
ተኝተው አገኛቸው ።
እስመ ክቡዳ አዕይንቲሆሙ በድቃስ ።
እንቅልፍ ጸንቶባቸዋልና ፤ በልተው ጠጥተዋልና ኃዘን ሰምተዋልና ።
፵፬ ወኀደጎሙ ወሖረ ካዕበ በሣልስት ወጸለየ ኪያሁ ከመ ቃለ እንዘ ይብል ።
፵፬ ሦስተኛ ሂዶ ያነኑ ጸለየ ለቀረበው ካዕበ ለመጀመሪያው ሣልስ አለ ። ሦስት ጊዜ መሆኑ የሦስትነት ቃሉ አለመለወጡ ያንድነት ምሳሌ ።
፵፭ ወእምዝ ገብአ ካዕበ ኀበ አርዳኢሁ ።
፵፭ ከዚህ በኋላ ሁለተኛ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሄደ ።
ወይቤሎሙ ኑሙ እንከ ወአእርፉ ።
ከእንግዲህስ ወዲህ ዕረፉ አላቸው፤ጊዜው ነውና ንሣእ ሀኪይ ሥጋየ መክፈልተከ እንዲል እንድም እኔ ከካስኩላችሁ ዕረፍት ነፍስ ዕረፉ ። እንድም ይሁዳ እራት ቤት ጭፍራ ይዞ የሚመጣ ነውና እያሳርፋችሁም እንጂ ካሳረፋችሁስ ዕረፉ ለማለት ። ናሁ በጽሐ ጊዜሁ ወያገብዕዎ ለወልደ ዕጓለ እመ ሕያው ውስተ እደ ኃጥአን ።
እነሆ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ በኃጥእን እጅ የሚያዝበት ጊዜ ደርሷል አላቸው ።
፵፮ ተንሥኡ ንሑር ናሁ በጽሐ ዘያገብአኒ ።
፵፮ የሚያሲዘኝ ይሁዳ እነሆ መጥቷል ተነሡ እንሂድ አላቸው ።
ዘከመ አግብአ ይሁዳ ለክርስቶስ ወዘከመ ተአኅዘ
፵፯ ወእንዘ ዘንተ ይትናገር ናሁ በጽሐ ይሁዳ ዘያገብእ እም፲ቱ ወ፪ቱ ፩፮ ማር ፲፬ ፡ ፵፫ ሉቃ ፲፪ ፡ ፵፯ ዮሐ ፲፰ ፡ ፫ ።

፵፯ ይህን ሲናገር ካሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ ሊያሲዘው መጣ ወመጽኡ ምስሌሁ ብዙኃንስ ሰብእ በመጣብሕ ወበአብትር እምኀቤሆሙ ለሊቃነ ካህናት ወለሊቃናተ ሕዝብ ።
ሾተል ጎመድ የያዙ ብዙ ሰዎች ሊቃነ ካህናት ዘንድ ከሱ ጋራ መጡ ሐተታ፤ እምስት ገበያ ሰው ይከተሰዋል አግባ መልስ ብሎ ቢጣላንሳ ብለው አሳቸው ከጲላጦስ ዘንድ ይዘው ይመጣሉ እሱ ከነሱ ተቀብሎ ይዞ መጥቷልና ፤

፵፰ ወዘያገብአ ወሀቦሙ ትእምርተ እንዘ ይብል ዘሰዓምኩ ውእቱ ኪያሁ አኃዙ ።

፵፰ የሚያሲዘው ይሁዳ የምስመው እሱ ነው እሱን ያዙ ብሎ ምልክት ሰጣቸው ፤ እንድም የሚሲዝበትን ምልክት ነገራቸው ።

፵፱ ወቀርበ ይእተ ጊዜ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወሰዓሞ ወይቤሎ በሀ ረቢ ።

፵፱ ወደ ጌታ ቀርቦ መምህር ቢሰኘሀን ጥለኛ ሀን አያውለው አያሳድረው ብሎ እጅ ነሳው ፤ ሐተታ ከሱን ሌላ ቢሰኛ ጠበኛ አለው አያውለኝ አያሳድረኝ ሲያሰኘው ነው ።
፶ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ በእንተ ዝንቱኑ መጻእከ እርክየ ።
፶ ወዳጄ ትእምርተ ፍቅሩን ትእምርተ ጸብእ አድርገኸው መጣሀን አለው ።
ወእምዝ ቀርቡ ወእንሥኡ እደዊሆሙ ወአሐዝዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
እጃቸውን አንስተው ማለት ጌታን አጽንተው ያዙት ።
፶፩ ወናሁ ተንሥእ እምእለ ምስሌሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ሰፍሐ እዴሁ ወመልሐ መጥባሕቶ ወዘበጦ ለገብረ ሊቀ ካህናት ።
፶፩ ከጌታ ጋራ ካሉት አንዱ ተነሥቶ ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መታው ።
ወመተሮ ዕዝኖ ዘየማን ፤
ቀኝ ጆሮውን ቆረጠው ፤ ትፈቅድኑ ንዝብጦሙ ብለውታል በሉቃስ አብሮ መብላት አብሮ ለመሞት እንጂ ነው እንበላቸው እንበላቸው ተባብለዋል ። እሱ ፈጣን ነውና መታው ቀኝ ጆሮውን ቆረጠው ከመታው አንገቱን አይለውም ቢሉ የካህን እጅ አያቀናምና ላንገቱ ያለው ለጆሮው ሆነ ። እንድም አንገቱን ብሎት ቢሆን በሞተ ነበር የጌታም ሞት ርትዕ በተባለ ነበርና ጆሮውንሳ ቢሉ በተአምራት ቀጥሎ ለታል ፤ ጆሮ የቀጠለ አንገት መቀጠል ይሳነዋልን ብሎ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ትንቢት ለትትቀረጽ ይእቲ ዕዝን እንተ ኢትሰምእ ለውእቱ ነቢይ ተብሎ ተነግሯል ፤ ምሳሌም ወለእመ አጥረ ይከ ገብረ ዕብራዌ ቅንየ ስድስተ ዓመተ ወበሳብዕ ዓም አግዕዞ በከንቱ ፤ ዕብራዊ ባሪያ ቢኖርህ በደመወዝ ገዝተህ በሰባተኛው ዓመት ገንዘብ ሳትስጥ

ነጻ አውጣው ትላለች አሪት ፤ እሱ ግን የጌታዬ ባሕርዩ ተስማምቶኛል የመቤቴ እንጀራዋ ወጧ ጣፍጦኛል ነጻ መውጣቱ ይቅርብኝ ያለ እንደሆነ ከቤተ እግዚአብሔር ወስደህ ከመድረኩ አስተኝተህ ጆሮውን ተርትረህ አፍንጫውን ስቀረህ እስከ ዕለተ ሞቱ ግዛው ትላለች አሪት ፤ እንደዚህም ሁሉ በሰባተኛው ሽህ ስዲያብሎስ ከመገዛት ላወጣችሁ መጥቼ ነበር እናንተ ካላችሁ በሥጋችሁ ቁማር በነፍሳችሁ ዲያብሎስ ይመልጥንባችሁ ለማለት፤ ያውስ ቢሆን ግራይቱ አለመሆኑዋ ቀኝቱ መሆኑዋ ስለምን ቢሉ ከነገደ ይሁዳ የተወለዱ ቀኝ ቀኝ አካላቸውን እየተቀቡ መንግሥትን ከነገደ ሌዊ የተወለዱ ቀኝ ቀኝ አካላቸውን እየተቀቡ ክህነትን ገንዘብ ያደርጉ ነበር ክህነትንም መንግሥትንም እንዳሳለፈባቸው ለማጠየቅ በቀኝ ጆሮው ምትረትን አፀዘበት ።

፶፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አግብእ ለመጥባሕትከ ውስተ ቤታ ዘፍ ፱ ፥ ፮ ራዕ ፲፫ ፥ ፲ ።

፶፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን ሾተልህን ወደ አፎት ቀጣህን ወደ ትዕግሥት መልስ አለው ።
እስመ ኲሎሙ እለ መጥባሕተ ያነሥኡ በመጥባሕት ይመውቱ ።
በሾተል የገደሉ ሁሉ በሾተል ይሞታሉና ።

፶፫ ይመስለከኑ ዘኢይክል አስተብቍዖቶ ለአቡየ ከመ ይፈኑ ሊተ ዘይበዝኅ እም፲ወ፪ቱ ሠራዊተ መላእክት ።

፶፫ ካሥራ ሁለቱ ነገደ መላእክት የሚበዙትን ይልክልኝ ዘንድ አባቴን መለመን መማለድ የማይቻለኝ ይመስላችኋልን ፤

፶፬ ወባሕቱ እፎ ይትፌጸም ወይበጽሕ ቃለ መጽሐፍ ዘይቤ ። ኢሳ ፶፫ ፥ ፲ ።

፶፬ ነገር ግን መጽሐፍ የተናገረው እንደምን ይደርሳል ይፈጸማል እኔ ካልሞትኩ ሲል ነው ።
እስመ ከመዝ ሀለዎ ይኩን ።
ይህ ይደረግ ዘንድ አለውና ።

፶፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለሕዝብ ሶበዝ ከመ ሠራቂኑ ትዴግኑኒ መጻእክሙ በመጥባሕት ወበአብትር ተአኃዙኒ ። ሰቆ ኤር ፬ ፥ ፳ ማር ፲፬ ፥ ፵፰ ሉቃ ፳፪፥፶፪ ዮሐ ፲፰ ፥ ፳፩ ።

፶፭ ሌባን እግባ መልስ ብሎ ቢጸላንሳ ብለው ሾተል ጎመድ ይዘው በትኩስ ፍለጋ እንዲፈልጉት ሾተል ጎመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁን አላቸው ።
ወዘልፈ እነብር ምስሌክሙ በምኲራብ ወእሜህር ዘመትር በምኲራብ ከናንተ ጋራ ሳስተምር እኖር ነበር ወኢፈ እንከ ኢአኃዝክሙኒ ።
ለምን አልያዛችሁኝም ።

፶፮ ወዝ ኲሉ ዘኮነ ከመ ይብጻሕ ወይትፌጸም ቃለ ነቢያት ።

፶፮ ይህ ሁሉ የተደረገ ነቢያት የተናገሩት ነገር ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው ።
ወእምዝ ኃደግዎ ኲሎሙ አርዳኢሁ ወጐዩ ።
ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጥለውት ሸሹ ።

ዘከመ ቆመ ኢየሱስ በቅድመ ዓውድ ።

፶፯ ወእለ አኃዝዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ወሰድዎ ኀበ ቀያፋ ሊቀ ካህናት ይትጋብኡ ጸሐፍት ።

፶፯ ወሊቃናት ። ጌታን የያዙት ግን ሽማግሎች ወደ ተሰበሰቡበት የካህናት አለቃ ቀያፋ ወዳለበት ይዘውት ሄዱ ፤

፶፰ ወተለዎ ጴጥሮስ እምርኁቅ እስከ ዓፀደ ሊቀ ካህናት ።

፶፰ ጴጥሮስ እስከ ካህናት አለቃ ቦታ ድረስ በሩቅ ተከተለው ።
ወቦአ ውሥጠ ወነበረ ምስለ ወዓልት ይርአይ ማኅለቅቶ ለነገር ።
የነገሩን ፍጻሜ ያይ ዘንድ እንዱን ቅጽር ገብቶ ተቀመጠ ፤

፶፱ ወየኃሥሡ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ወሊቃናት ወኲሉ ዓውድ ሰማዕተ ሐሰት በዘይስቅልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፶፱ ጸሐፍትና የካህናት አለቆች ሽማግሎችም ጌታን በሚገሉበት ነገር ይገሉት ዘንድ የሐሰት መሳክርት ይሹ ነበር ።

፷ ወኢረከቡ ሎቱ ጌጋየ ።

፷ አላገኙበትም ።
ወመጽኡ ብዙኃን ሰማዕተ ሐሰት ።
ብዙ የሐሰት ምስክሮች መጡ ወሰአኑ ቦቱ ነገረ ።
መርታት ተሳናቸው ማለት ነውር አጡበት ።
ወድኅረ መጽኡ ፪ቱ ።
ከዚህ በኋላ ዕውነተኞች ናቸው የሚባሉ ሁለት ሰዎች መጡ ።

፷፩ ወይቤሉ ይቤ ዝንቱ እክል ነሚቶቶ ለቤተ እግዚአብሔር ወበሣልስት ዕለት አኀንጾ ፥ ዮሐ ፪ ፥ ፲፱

፷፩ ይህ ቤተ መቅደስን አፍርሼ በሦስተኛው ቀን እንጸዋለሁ አለ አሉ ።

፷፪ ወተንሥአ ሊቀ ካህናት ወይቤሎ ኢትሰ ምዕኑ እንዘ መጠነዝ ያስተዋድዩከ አሉ ።

፷፪ ሊቀ ካህናቱ ተነሥቶ ይህን ያህል ሲያጣሉህ ሲያካስሱህ አትሰማምን አለው ።

፷፫ ወኢያውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ፤

፷፫ ጌታ አልመለሰለትም ፤ ሐተታ ነገሩ ተርታ ቢሆንበት እንዳልፈራ ለማጠየቅ እንዳይቀርለት ያውቃልና ለጥብዓት ለትዕግሥት አብነት ለመሆን ።
ወይቤሎ ሊቀ ካህናት አመሐልኩከ በእግዚአብሔር

ሕያው ከመ ትንግረኒ እመ አንተሁ ውእቱ ክርስቶስ ወልዱ ለእግዚአብሔር ።
እስከ ክርስቶስ ተብሎ የተነገረልሀ የሕያው የእግዚ አብሔር የባሕርይ ልጁ አንተ እንደሆንክ ትነግረኝ ዘንድ በሕያው እግዚአብሔር አማጽኜሀለሁ አለው ።

፷፬ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አንተ ትቤ ። ማቴ.፲፮ ፥ ፳፯ ሮሜ ፲፬ ፥ ፲ ፥ ፩ ተሰሎ ፬፥፲፮ ።

፷፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ትላለህ አለው ።
ወባሕቱ እብለክሙ እምይእዜሰ ትሬእይዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዘ ይነብር በየማነ ኃይል ።
ነበረ ካልኩ ብሎ የማን ብሏል እንጂ በክብር ሲል ነው ከእንግዲህስ ወዲህ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን በአብ ዕሪና ታዩታላችሁ ፣ አንድም በየማን ኃይል ዓለምን በማሳለፍ ኃይል ፣ ባለው ዕሪና ። ወይመጽእ በደመና ሰማይ ። በባሕርይ ክብሩ መጥቶ ታዩታላችሁ ። ሐተታ የደብረ ታቦር የዕርገት የምጽአት ደመና የባሕርይ ክብሩ ነው ። አንድም በሥጋ ማርያም መጥቶ ፣ ሰማይ ዳግሚት እንዲል ፣ አንድም በክበበ ትስብእት መጥቶ ።

፷፭ ወሠጠጠ አልባሲሁ ሊቃነ ካህናት ።
፷፭ በገዛ እጁ ፈጣሪዩን ላሰድብ ብሎ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀደደ ። ሐተታ በኃዘን ምክንያት ልብሱን የቀደደ ፊቱን የነጩ እንደሆነ ይሻር ትላለች እሪት ፣ ጌታ እንደ ተሾመበት እሱ እንደተሻረ ለማጠየቅ ፣ እንዘ ይብል ምንተ እንከ ትፈቅዱ ሎቱ ሰማዕተ ።
ምን ምስክር ትሹለታላችሁ ፣ ናሁ ጸረፈ ።
ይሳደባል ማለት እነሆ አምላክ ነኝ አለ ።
ወሰማዕክሙ ጽርፈቶ ።
አምላክ ነኝ ሲል ሰምታችኋል ፤

፷፮ ምንተ እንከ ትብሉ ።ኢሳ.፶፡፯ ። ማር፡፲፬፡፷፬
፷፮ ምን ትፈርዳላችሁ ፤
ወአውሥኡ ወይቤሉ ዝንቱ ድልው ለሞት ።
ይህ ሞት ይገባዋል አሉ ።
፷፯ ወእምዝ ተፍኡ ውስተ ገጹ ።
፷፯ ከዚህ በኋላ በፊቱ ተፉበት ፣ ወይትህ ከዩ ወሪቀ ውስተ ገጽየ ።
ወኢሜጥኩ ገጽየ እምኃፍረተ ምራቅ ያለው ትንቢት ሊደርስ ሊፈጸም ። አንድም አዳምን ዲያብሎስ በገጸ ልቡናው ምራቀ ምክሩን እየተፋ ከገሃነም አውርዶት ነበርና ለሱ ካሣ ሊሆን ።
፷፰ ወኰርዕዎ ።
፷፰ ራሱን በዘንግ መቱት ። ወዘሎ ርእስ ለሕማም ያለው ትንቢት ሊደርስ ሊፈጸም ። አንድም ዲያብሎስ የአዳምን ርእሰ ልቡናውን በዘንግ እየመታ ገሃነም አውርዶት ነበርና ካሣ ሊሆን ።
ወጸፍዕዎ ።
ፊቱን በሻሽ ሸፍነው መቱት እንዘ ይብሉ መኑ ውእቱ ክርስቶስ ዘጸፍዓከ ።
ክርስቶስ በጥፊ የመታህ ማነው ንገረን እያሉ ፣ ሐተታ፤አዳምና ሔዋን የእምላክነት ዕውቀት እን ወቅ ብለው ገሐነም ወርደው ነበርና ለሳቸው ካሣ ሊሆን ።

በእንተ ክህደተ ጴጥሮስ ።

፷፱ ወጴጥሮስ ሀሎ ይነብር አፍአ ውስተ ዓጸድ ሉቃ.፳፪፡፶፭፡፸ ፤ ዮሐ. ፲፰ ፥ ፲፯ ።

፷፱ ጴጥሮስ ግን አንዱን ቅጽር ገብቶ ተቀ ምጦ ነበር ፤
ወመጽአት ኀቤሁ አሐቲ ወለት ወትቤሎ አንተሂ ምስለ ኢየሱስ ገሊላዊ ሀለውከ ።
አንዲት ብላቴና መጥታ አንተም ከገሊላዊ ከኢየሱስ ጋራ ነበርክ አለችው ።

፸ ወክህደ በቅድመ ኵሉ ሕዝብ እንስ ኢየ አምሮ ዘትብሊ ።
፸ የምትዪውን አላውቀውም ብሎ በጉባኤ ካደ ።

፸፩ ወወፂአ ኆኅተ ርእየቶ ካልዕት ወለት ።
፸፩ አንዱን በር ወጥቶ ሳለ ሌላዪቱ አየችው ። ወትቤሎሙ ለእለ ይቀውሙ ዝኒ ሀሎ ምስለ ኢየሱስ ናዝራዊ ።
ተቀምጠው ላሉት ይህም ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋራ ነበር አለቻቸው ።
፸፪ ወክህደ ካዕበ ።
፸፪ ሁለተኛ ካደ ።
ወመሐለ ከመ ኢየአምሮ ለውእቱ ብእሲ ።
ያን ሰው እላውቀውም እንዳላውቀው ብሎ ማለ ፣
፸፫ ወጐንድዮ ሕቀ መጽኡ እለይቀውሙ ።
፸፫ ጥቂት ቆይቶ የተቀመጡት መጡ ።
ወይቤልዎ ለጴጥሮስ አማን አንተሂ እምኔሆሙ ።
አንተም በውነት ከሳቸው ወገን ነሀ አሉት ።
ወነገርከ ያዔውቀከ ።
ባነጋገርህ ትታወቃለሀ ።
፸፬ ወእምዝ መሐለ ወተረግመ ከመ ኢየአ ምሮ ለውእቱ ብእሲ ።
፸፬ የያዘውን ጥሎ እንዲህ ይጣለኝ የሱን ሞት ለኔ ያድርገው ያን ሰው አላውቀውም ብሎ ማለ ።
፸፭ ወተዘከረ ጴጥሮስ ቃሎ ለእግዚእ ኢየሱስ ዘይቤሎ ሥልሰ ትክህደኒ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ።
፸፭ ጴጥሮስም ጌታ ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለውን አሰበ ።
ወወፅአ አፍአ ወበከየ ብካየ መሪረ ።
ከአፍአ ወጥቶ ጽኑ ኃዘን አዘነ ፤ ሐተታ ከሁሉ ይልቅ እኔ እወደው ከሁሉ አስቀድሞ እኔ አከደው ብሎ አዘነ ። የአዳም የዳዊት የቅዱስ ጴጥሮስ ሐዘን አንድ ነው ሳይሰቀቁ ዕንባቸው እንደሰን ውኃ ይወርዳል ።

ምዕራፍ ፳፯ ።

፩ ወጸቢሖ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት ወሊቃናተ ሕዝብ ይቅትልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፩ ሲነጋ በነጋ ጊዜ የካህናት አለቆች የሕዝቡም አለቆች ጌታን ሊገድሉት እንግደለው ብለው መከሩ ።

፪ ወአሰርዎ ወሰድዎ ወመጠውዎ ለጲላጦስ መኰንን ማር. ፲፭ ፥ ፩ ሉቃ ፳፫ ፥ ፩ ዮሐ. ፲፰ ፥ ፳፰ ።

፪ አሰረው ወሰደው ለጲላጦስ ሰጡት ሐተታ አዳምን ለመኰንን ገሃነም አሳልፎ ሰጥቶ ነበርና ለዚህ ካሣ ሊሆን ።

በእንተ ቀቢጸ ተስፋ ዘይሁዳ ።

፫ ወእምዝ ሶበ ርእየ ይሁዳ ዘአግብኦ ከመ አሰርዎ አግብአ ውእተ ፴ ብሩረ ለሊቃነ ካህናት ወለሊቃውንተ ሕዝብ ።

፬ እንዘ ይብል አበስኩ ዘአግባእኩ ደመ ንጹሐ ወአቅተልኩ ብእሴ ጻድቀ ።

፫ ከዚህ በኋላ ያሲያዘው ይሁዳ አሰርሀዎ እንዳሰሩት አርስሀዎ ጎጥእ ብለው እንደፈረዱበት ከመ ረሲዕ ወከመ ተኰነነ ጎጥእ ተብሎ እንደተፈረደበት ፤

፬ ባየ ጊዜ ኦሪት ኢትቅትል ብእሴ ጻድቀ ያለችውን አፍርሼ ንጹሕ ደም ያስፈሰስኩ ደግ ሰው ያስገደልኩ አሳልፌም ብሎ ያን ሠላሳ ብር ለሊቃነ ካህናት ለሕዝብ አለቆች መልሶ ወሰደ ሰጠ ፤ ሐተታ እሱም በተአምራቱ ይድናል እኔም ገንዘቡን እንደ ያዝሁ እተርፋለሁ ብሎ ሸጦት ነበርና ።

ወይቤልዎ ሚ ላዕሌነ ወሚ ላዕሌከ ።
ይሁዳ የመረጥነውን ሰጠኸን የወደድከውን ሰጠንህ ከእንግዲህ ወዲህ ላንተ ከኛ ምን አለህ ለኛስ ካንተ ምን አለን ።
ለሊከ አእምር ለርእስከ ።
አንተ ለራስህ ዕወቅ አሉት ።

፭ ወገደፈ ውእቱ ብሩረ ውስተ ምኵራብ
ወሖረ ወተሐንቀ ወሞተ ግብ. ሐዋ. ፩ ፥ ፲፰ ።

፭ ያን ብር ከምኵራብ ደጅ አፍሶት ሄዶ ታንቆ ሞተ ፤

፮ ወነሥኡ ሊቃነ ካህናት ውእተ ብሩረ ወይቤሉ ኢይደልወነ ንደዮ ውስተ ወርቀ መባዕ እስመ ሤጠ ደም ውእቱ ፤

፮ ሊቃነ ካህናት ያን ብር አንሥተው የደም ዋጋ ነውና ከመባዕ ልንጨምረው አይገባንም አሉ ። ሐተታ ፤ በሀገራቸው የደም ዋጋ ሤጠ ከልብ አስበ ደነስ ከመባዕ አያገቡም ነበርና ።

፯ ወተማከሮሙ ተሣየጡ ቦቱ ገራኅተ ለብሐዊ ለመቃብረ እንግዳ ፤

፯ ለመጣተኛ ለስደተኛ መቀበሪያ ሊሆን መከረው ቦታ ገዙበት ሐተታ ፤ ከጣእት ከኃጢአት ፈልሶ ለመጣ መከበሪያ ሊሆን ምእመናን ጥምቀትን ገንዘብ ማድረጋቸውን መናገር ነው ፤

፰ ወተሰምየ ውእቱ ገራኅት ገራኅተ ደም እስከ ዮም ፤ ግብ. ፩ ፥ ፲፱ ።

፰ ያ ቦታ እስካሁን ድረስ የደም ምድር ሲባል ይኖራል ።

፱ ወይእተ አሚረ በጽሐ ቃለ ኤርምያስ ነቢይ ዘይቤ ነሥኡ ፴ ብሩረ ሤጦ ስክቡር ዘአክበርዎ እምደቂቀ እስራኤል ወወሀብዎ ለገራኅተ ለብሐዊ ዘካ. ፲፩ ፥ ፲፪ ፤

፱ ደቂቀ እስራኤል በሆሣዕና ያከበሩትን ከደቂቀ እስራኤል ተለይተው የከብርን ዋጋ ፤ አንድም ዘተከህሉ ይላል ደቂቀ እስራኤል የተስማሙበትን ለገራኅተ ለብሐዊ የሰጡትን የከብሩን ዋጋ ወሰዱ ብሎ ኤርምያስ የተናገረው ደረሰ ተፈጸመ ።

፲ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር ፤
፲ ወወሀብዎ ለገራኅተ ለብሐዊ ማለትን እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ እናገራለሁ አለ ፤ የማይገባ ማለት ነው ።
ዘከመ ቆመ እግዚእ ኢየሱስ ቅድመ ጲላጦስ ፤

፲፩ ወቆመ እግዚእ ኢየሱስ ቅድሜሁ ለመስፍን ማር. ፲፭ ፥ ፪ ሉቃ. ፳፫ ፥ ፫ ዮሐ. ፲፰ ፥ ፴፫ ።

፲፩ ጌታ ከጲላጦስ ፊት ቆመ ።
ወሐተቶ ወተስእሎ መስፍን ።
ጲላጦስ ጠየቀው ።
ወይቤሎ አንተኑ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።
የአይሁድ ንጉሣቸው አንተ ነህን አለው ።
ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አንተ ትቤ ።
አንተ ትላለህ አለው ። አንድም አንተ ያንድ መንደር ንጉሥ ታደርገኛለህ ።

፲፪ ወእንዘ ያስተዋድይዎ ሊቃነ ካህናት ወሊቃውንተ ሕዝብ አልቦ ዘያወሥአሙ ወኢምንተኒ ።
፲፪ የሕዝቡ አለቆችና የካህናት አለቆች ሲያሳጡት ሲያጣሉት ምንም ምን የመለሰላቸው ምላሽ የለም ።

፲፫ ወእምዝ ይቤሎ ጲላጦስ ኢትሰምዖኑ እንዘ መጠነዝ ያስተዋድዩከ ።
፲፫ ይህን ያህል ሲያሳጡህ ሲያከስሱህ አትሰማምን አለው ።

፲፬ ወኢያውሥአ ወኢአሐተኒ ቃለ ፤
፲፬ ጥቂት ስንኳን አልመለሰለትም ሐተታ እንዳሰፈው ።
እስከ ያነክር መልአክ ።
ጲላጦስ ይህን ያህል ትዕግሥት ብሎ እስኪያደንቅ ድረስ ።

ዘከመ ኀረይዎ ለበርባን እምነ ኢየሱስ ወከመ ኰነንዎ ።

፲፭ ወቦ ልማድ ለመስፍን ያሕዩ ለሕዝብ ፩ደ እምውስተ ሙቁሓን ዘፈቀዱ ።

፲፭ ከታሰሩት የወደዱትን ይፈታላቸው ዘንድ ለጲላጦስ ልማድ ነበረው ። አንድም በሙ ልማድ ይላል ባመት ባመት ለበዓለ ፋሲካ ክስር ቤት ገብ ተው የወደዱትን ይፈቱ ዘንድ ለሕዝቡ ልማድ ነበራቸው ።
ሐተታ፤በግብጽ ሳሉ ሁለት እስሮች ነበሯቸው እነ ዚያን ፈተው ይዘው ወጥተዋልና ፤ በግብጽ ሳሉማ ምን እስር ነበራቸው ብሎ በግብጽ መኖራቸውን እንደ መታሰር ፤ ከግብጽ መውጣታቸውን እንደ መፈታት አድርገውት በበዓል አንድ አንድ እስር ይፈቱ ነበርና በዚያ ልማድ ።

፲፮ ወቦ አሜሃ ሙቁሕ ዘስሙ በርባን ስሙዕ
፲፮ ያን ጊዜ በርባን የሚባል የታወቀ እስር ነበር ።
ወየአምሮ ኵሉ ።
ወንበዴ መሆኑን ሁሉ ያውቀዋል ።

፲፯ ወእንዘ ጉቡአን እሙንቱ ይቤሎሙ ጲላጦስ ለሕዝብ መኑ ትፈቅዱ አሕዩ ለክሙ ።
፲፯ እሳቸው ባንድነት ተሰብስበው ሳሉ ማን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ ?
በርባንሃኑ ።
በርባንን ነውን ።
ወሚመ ኢየሱስሃኑ ዘይብልዎ ክርስቶስ ።
ወይም ክርስቶስ የተባለ ኢየሱስን ነው አላቸው ።

፲፰ እስመ የአምር ከመ በቅንዓቶሙ አግብእዎ
፲፰ ጠልተው ተመቅኝተው ቀንተው ለሕማም ለሞት አሳልፈው እንደሰጡት ያውቃልና ።

፲፱ ወእንዘ ይነብር ጲላጦስ ዓውደ ለአከት ኀቤሁ ብእሲቱ ።
፲፱ ባደባባይ ተቀምጦ ነገር ሲሰማ ሚስቱ ላከችበት አብሮቅላ ትባላለች ።
እንዘ ትብል ኢቅእ ኢትእብስ ላዕለ ውእቱ ጻድቅ ።
ያን ደግ ሰው እንዳትበድል አስተውል ብላ ።
እስመ ብዙኀ ሐመምኩ በዛቲ ሌሊት በሕልምየ በእንቲአሁ በዚች ሌሊት በሱ ምክንያት በሕልሜ ብዙ ሥቃይ ሳይ አድሬአለሁና ። ሐተታ ምን ስታይ አድራለች ቢሉ እሱን ዘንዶ ሲውጠው እሷን በእ ሳት አለንጋ ሲገርፏት አይታለች ይህን ልካበታለች ፤ አብረው አድረው አልነበረም ቢሉ እነግረዋለሁ ስትል አንበሳ መዶብ ወጣ ሲመለስ እነግረዋለሁ ስትል ጨኸት ሰምቶ ወጣ በዚያው እንደወጣ ቀር ቷል ። አንድም ዶርታ መከራ የሚባሉ ከተወለዱ ጀምሮ ተናግረው ሰምተው የማያውቁ ልጆች ነበ ሯቸው ንጹሕ ደም ለሚያፈስ ለዚያ ለባልሽ ወዮለት ብለዋታል ይኸን ልካበታለች ።

፳ ሊቃነ ካህናትሰ ወሊቃውንተ ሕዝብ ጌጥዎሙ ለሕዝብ ወአሆ አበልዎሙ ከመ በርባንሃ ያሕዩ ሎሙ ይስአሉ ወኢየሱስሃ ይቅትሉ ማር ፣ ፲፭ ፣ ፲፩ ሉቃ ፳፫፣፲፰ ዮሐ ፲፰፣፵ ግብ፡ ሐዋ፡ ፫፡፲፬ ።

፳ የሕዝቡ አለቆችና ሊቃነ ካህናት ግን በር ባንን አድንልን ኢየሱስን ስቀልልን ብለው ይለምኑ ዘንድ ሕዝቡን አባበሏቸው እሽ በጁ አሰኙዋቸው ።

፳፩ ወአውሥአ መስፍን ወይቤሎሙ መኑ ትፈቅዱ እምክልኤሆሙ አሕዩ ለክሙ ።

፳፩ ጲላጦስ መለሰ ከሁለቱ ማናቸውን ላድን ላችሁ ትወዳላችሁ አላቸው ።
ወይቤሉ በርባንሃ ።
በርባንን ነው አሉ ።

፳፪ ወይቤሎሙ ጲላጦስ ምንተ እንከ እሬስዮ ለኢየሱስ ዘተብህለ ክርስቶስ ።

፳፪ ክርስቶስ የተባለ ኢየሱስን ምን አደር ገዋለሁ ። አንድም እረስዮ ይላል ምን ላድርገው አላቸው ።
፳፫ ወይቤሉ ኵሎሙ ስቅሎ ።
፳፫ ሁሉም ስቀለው አሉ ።
ወይቤሎሙ መስፍን ምንተ እኩየ ገብረ ።
ምን ክፉ ሥራ ሠራ አላቸው ።
ወአፈድፈዱ ጽራሃ እንዘ ይብሉ ስቅሎ ስቅሎ ።
ስቀለው ብንልህ ስቀለው አሉ ።
፳፬ ወእምዝ ሶበ ርእየ ጲላጦስ ከመ አልቦ ዘይበቁዕ ዘእንበለ ዳዕሙ ዘይበዝኅ ሀከክ ።
፳፬ ጸብዕ ክርክር እየጸና ከመሄድ በቀር የሚ ረባው የሚጠቅመው ነገር እንደሌለ ጲላጦስ ባየ ጊዜ ነሥአ ማየ ወተሐፅበ እዴሁ በቅድሜሁ ለሕዝብ እንዘ ይብል ንጹሕ አነ እምደሙ ለዝ ብእሲ ጻድቅ ። ውኃ አስመጥቶ በዚህ ሰው ደም ከመጣ ፍዳ ንጹሕ ነኝ ብሎ ባደባባይ እጁን ታጠበ በእዕሩገ እስራኤል ልማድ ፤ ታሪከ ከሀገርና ከሀገር መካከል ሰው ሙቶ የተገኘ እንደሆነ ያሰው ለሞተበት አቅራቢያ ለሚ ሆን አገር ሰዎች ውኃ በመንቀል ይዘው ጊደር ነድተው ከበረሃ ይወርዳሉ ቋንጃዋን ይመቷታል ትወድቃለች የዚህን ሰው ደም አላፈሰስንም ያፈሰሰውንም አላየንም ብለው ይታጠባሉ ከገ ዳዩ ወገን ሲደርስ መወየብ ይጀምራል እሱ ሲሆን ፈጽሞ ደም ይሆንበታል ፤ ምእመናን ጥም ቀትን ገንዘብ ማድረጋቸውን መናገር ነው ።
አንትሙ ለሊክሙ አእምሩ ።
እናንት ለራሳችሁ ዕወቁ ።
፳፭ ወአውሥኡ ኵሉ ሕዝብ ወይቤሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ ፤

፳፭ ደሙ በኛም በልጆ ልጆቻችንም ይሁን አሉ ፤ ሐተታ እንዲህ ብለው የተናገሩበት እንደበ ታቸው የሚሸት የሚከረፋ ሁነዋል ልጆቻቸውም ወንድ የሆነ እንደሆነ በጁ ደም ጨብጦ ባፉ ደም ጎርሶ የሚወለድ ሁነዋል ሴት የሆነች እን ደሆነ በተፈትሆ የምትወለድ ሁናለች ።

፳፮ ወእምዝ አሕየወ ሎሙ በርባንሃ ።
፳፮ ከዚህ በኋላ በርባንን ፈታላቸው ።
ወቀሥፎ ለእግዚእ ኢየሱስ ወመጠዎሙ ይሰቅልዎ **ጌታን ገርፎ** ስቀሉ ብሎ ሰጣቸው ። ሐተታ ካልቀረበ [illegible] ይበላቸው ብሎ ። አንድም ራርተው ይቂውታል መስሉት ። አንድም ወመጠውኩ ዘባንየ ለቅሥፈት ያለው ትንቢት ሊደርስ ሊፈጸም አን ድም ዲያብሎስ የአዳምን ዘባን ልቡናውን እየገረፈ ገዥነም አውርዶት ነበርና ለዚያ ካሳ ሲሆን አንድም በጌታ የግፍ ድርብ ይደረግበታልና ለልማዱ የሚ ሰቀል አይገረፍም የሚገረፍ አይሰቀልም ነበር ። እሱን ግን ገርፈው የሚሰቅሉት ነውና ።

ዘከመ ተሣለቁ በላዕለ ኢየሱስ ።

፳፯ ወእምዝ መስተራትዓተ ሐራ ነሥእዎ ለእ ግዚእ ኢየሱስ እምውስተ ዓውድ ወወሰድዎ ኀበ ምኵናን ። መዝ ፳፩ ፡ ፲፮ ማር ፲፭ ፡ ፲፮ ።

፳፯ ከዚህ በኋላ ጭፍራውን የሚመሩ የሚያ ቅናኑ ካደባባይ ወደሚፈረድበት ቦታ ይዘውት ሄዱ ። ሐተታ፡ቤተ እንሳ ቤተ አጼቸ ባለወንች የሚባሉ ሲቃይ ቀራጭ ባለወንች በቤተ መንግሥት እንዳሉ ። ወአስተጋብኡ ኵሎ ሠርዌ ሐራ አለቆች ጭፍራ ቸውን ሰበሰቡ አንድም ኵሎ ሠርዌ ሐራ ጭፍሮች አለቆችን ፤ አንድም ወአስተጋብኡ ኵሎ ሠርዌ ሐራ ብለህ እናበህ ፤ ጭፍሮች ያሏቸው አለቆች ሕዝ ቡን ሰበሰቡ ።
ወሰለብዎ አልባሲሁ ።
ልብሱን ገፈፉት ።
ሐተታ፤የአዳም ልጅነት እንደሄደበት ያጠይቃል ።

፳፰ ወአልበስዎ ከለሜዳ ዘለይ ።

፳፰ ቀይ ግምጃ አለበሱት ፤ ደምህ ይፈሳል ሲሉ ። አንድም ደማችንን ባርባ ዘመን በጥጦስ ታፈስዋለህ ሲሉ ።

፳፱ ወጸፈሩ ሐራ አክሊለ ዘሦከ ወአስተቀ ጸልዎ ዲበ ርእሱ ። ዮሐ ፲፱ ፡ ፪

፳፱ ጭፍሮች የሾህ አክሊል ታተው ደፋለት ሐተታ፡እነገሥንህ ብለውታልና በፍና ተሣልቆ ። አንድም ወወደዩ ጌራ መድኃኒት ዲበ ርእሱ በአክ ሊል ዘአስተቀጸለቶ እሙ ያለው ትንቢት ሊደርስ ሊፈጸም ድርሳነ መድኃኔ ዓለም ሾህ ቀቃቅን ስባ ታላላቅ እሾህ ያለው የብረት ዘውድ ነው ይላል እንደምን ነው ቢሉ ነገር እንደዚህ ነው ያስ ቢሆን ኢትስብሩ ዓፅሞ ያለው በፈረሰ ነበር ።

ወአስተአኀዝዎ ህለተ ውስተ የማኑ ።
በቀኝ እጁ ዘንግ አስያዙት እነገሥንህ ብለውታልና በፍና ተሣልቆ ፤ አንድም ብርዒ ይላል አብነት ፤ ብርዕ አስያዙት ሥራ ፈት ነህ ሲሉ ጽሕፈትንማ ርእስ ጥበብት እንጅ ይለዋል ብሎ ኃጢአታችንን በፍዳ ታጽፍብናለህ ሲያሰኛቸው ነው ።
ወአስተብረኩ ቅድሜሁ ፤
ሰገዱለት ፤
ወተሣለቁ ላዕሌሁ ፤
ዘበቱበት ፤
ወይቤልዎ በሀ ንጉሠ አይሁድ ፤
የአይሁድ ንጉሣቸው ቢሰኘሀን ጠበኛሀን አያውለው አያሳድረው አሉት ከነሱ ሌላ ቢሰኘ ጠበኛ አለውን አያውለን አያሳድረን ሲያሰኛቸው ነው ።

፴ ወይወርቁ ላዕሌሁ ።
፴ በፊቱ ተፉበት ።
ሐተታ እንዳለፈው ።
ወነሥኡ ህለተ ወኰርዕዎ ርእሶ ።
ያስያዙትን ዘንግ ተቀብለው ራሱን መቱት ፤ ሐተታ እንዳለፈው

፴፩ ወተሣለቁ ላዕሌሁ ሰለብዎ ውእተ ከለ ሜዳ ዘለይ ፤

፴፩ ከዘበቱበት በኋላ ያለበሱትን ቀይ ግምጃ ገፈፉት ።
ወአልበስዎ አልባሲሁ ።
የጥንት ልብሱን አለበሱት የአዳም ልጅነት እንደ ተመለሰለት ያጠይቃል ።
ወወሰድዎ ይሰቅልዎ ።
ሊሰቅሉት ይዘውት ሄዱ ።

፴፪ ወእንዘ ይወጽኡ ረከቡ ብእሴ ቀሬናዌ ዘስሙ ስምዖን እትወቶ እምሐቅል ። ማር ፲፭ ፡ ፳፩ ሉቃ ፳፫ ፡ ፳፮ ።

፴፪ ሊሰቅሉት ይዘውት ሲሄዱ ስምዖን የሚ ባል የቀሬንዮ ሰው ከተሠወረበት ሲመለስ አገኙ ፤
ወአበጥዎ ይጹር መስቀሎ ፤
መስቀሉን ይሸከም ዘንድ ጎተቱት ፤ ሐተታ ነገር ፈርቶ ተሰውሮ ውሏል ነገር ተፈጽሟል ብሎ ሲወጣ አገኙት አንተም የሱ ወገን ነህ መስቀሉን ተሸከም ብለው አሸከመውታል ፤ ምሥጢሩ ግን ጌታ ከበ ረከተ መስቀሉ እንዳሳተፈው ያጠይቃል ፤

፴፫ ወበጺሖሙ ብሔረ ዘስሙ ጎልጎታ ዘበ ትርጓሜሁ ቀራንዮ ። ማር ፲፭ ፡ ፳፪ ሉቃ ፳፫ ፡ ፴፫ ፡ ዮሐ ፲፱ ፡ ፲፯ ።

፴፫ ባንዱ ልሳን ቀራንዮ ወደሚሉት ጎልጎታ በደረሱ ጊዜ ።

፴፬ ወወሀብዎ ይስተይ ወይነ ወሐሞተ ድሙረ ፤

፴፬ ሐሞት የተቀላቀለበት ወይን ይጠጣ ዘንድ ሰጡት ፤

ወጥዒሞ አበየ ሰትየ ።
ቀምሶ አልጠጣም አለ ።

ዘከመ ተሰቅለ ኢየሱስ

፴፭ ወእምዝ ሰቀልዎ ማር ፲፭ ፡ ፳፬ ሉቃ ፳፫ ፡ ፴፫ ዮሐ ፲፱ ፡ ፳፫ ፡ መዝ ፳፩ ፡ ፲፱ ።

፴፭ ከዚህ በኋላ ሰቀሉት ።
ወተካፈሉ አልባሲሁ እንዘ ይትዓፀው ።
ልብሱን በዕፃ ተካፈሉ ፤
በከመ ጽሑፍ ወተካፈሉ አልባስየ ለርእሶሙ ወተዓፀው ዲበ አራዝየ ተብሎ በነቢይ እንደ ተጻፈ ፤

፴፮ ወነበሩ የዓቅብዎ ሀየ ፤
፴፮ ሲጠብቁት ዋሉ ፤
፴፯ ወአንበሩ መልዕልተ ርእሱ ጽሒፎሙ መጽሐፈ ጌጋዩ ዘይብል ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሦሙ ለአይሁድ ፤

፴፯ የናዝሬቱ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሣቸው ነው የሚል በደሉን የሚነግር ደብዳቤ ከራሱ በላይ ከመስቀሉ ትርፍ ጠርቀው ተውት ፤

፴፰ ወእምዝ ሰቀሉ ምስሌሁ ፪ተ ፈያተ ፤
፴፰ ከዚህ በኋላ ሁለት ወንበዶች ከሱ ጋራ ሰቀሉ ፤
አሐደ በየማኑ ፤
አንዱን በቀኙ ፤
ወአሐደ በፀጋሙ ፤
አንዱን በግራው አነገሥንህ ብለውታልና በፍና ተሣልቆ ፤ ሐተታ ቀኛዝማችና ግራዝማች ቢትወደድ ግራ ቢትወደድ ሾምንልህ ሲሉ አንድም ለማሳሳት በቀኝ በግራ የመጣው ያ ምንድነው ወንበዴ ይሉታል ያሳ የመካከለኛው ይላል ያስ ከዚህን ልዩ ነው ለማለት አንድም ተኈለቆ ምስለ ጊጉያን ያለው ትንቢት ሊደርስ ሊፈጸም ፤ ይህንም ሊቁ ከመ ይደምረነ ምስለ ነፍሰ ጻድቃን ብሎ ተርጉሞታል ምሥጢሩን ግን እኛን ኃጥአንን በግራ ታቆመናለህ ሲያስኛቸው ነው ፤

፴፱ ወእለሂ የኃልፉ ይፀርፉ ላዕሌሁ እንዘ የሐውሱ ርእሶሙ ፤

፴፱ የሚያልፉ የሚያገድሙት ራሳቸውን እየ ነቀነቁ ይሰድቡት ነበር ።

፵ ወይብሉ አ ዘይነስቶ ለቤተ መቅደስ ወየሐንጾ በሣልስት ዕለት አድኅን ርእሰከ ዮሐ ፪ ፡ ፲፱ ።

፵ ቤተ መቅደስን አፍርሰህ በሦስተኛው ቀን እሰራዋለሁ የምትል ራስህን አድን እያሉ ።
እመሰ አማን ወልደ እግዚአብሐር አንተ ረድ እመ ሰቀልከ ።
የእግዚአብሐር ልጅ ከሆንክ ከመስቀልህ ውረድ ።

፵፩ ወከማሁ ሊቃነ ካህናት ይሣለቁ ምስለ ጸሐፍት ወሊቃናት ።

፵፩ እኒያ እንደሰደቡት ሊቃነ ካህናትም ከጸሐፍትና ካስቆች ጋራ ሰደቡት ።

፵፪ እንዘ ይብል ባዕደ ያድኅን ወርእሶ ኢይክል አድኅኖ ፤

፵፪ ሌላውን ያድናል ራሱን ማዳን አይቻለውም እያሉ ። ማቴ ፪ ፡ ፲፰ ።
እመሰ ንጉሠ እሥራኤል ውእቱ ለይረድኬ ይእዜ እምነ መስቀሉ ንርአይ ወንእመን ቦቱ ። የእሥራኤል ንጉሥ ከሆነ ከመስቀሉ ይውረድና አይተን እንመንበት ። ሐተታ ወርዶም ቢሆን ፈርቶ ነው ባሉ ነበር እንጂ ባላመኑትም ነበር ። ሶበሰ ወረደ እግዚእነ እምነ መስቀሉ እመርሀ ከመ ውእቱ ፈርሀ እሞት እንዲል ።

፵፫ እመሂ ተአመነ በእግዚአብሐር ናሁ ይእዜ ያድኅኖ ፤ መዝ ፳፩ ፡ ፰ ።

፵፫ በእግዚአብሐር ከታመነ ማለት የእግዚአብሐር ልጅ ከሆነ እነሆ ዛሬ ያድነው ።
አመ ይፈቅዶ ።
ሰንኳን ይወልደው ይወደው እደሆነ ።
እስመ ይብል ወልደ እግዚአብሐር አነ ።
የእግዚአብሐር ልጅ ነኝ ይላልና ።

፵፬ ወከማሁ ፈያትኒ እለ ተሰቅሉ ምስሌሁ ይዘነጕግዎ ።

፵፬ እነዚያ እንደሰደቡት ከሱ ጋራ የተሰቀሉ ወምበዶችም ሰደቡት ፈያታይ ዘየማንም ቢሉ ፀሐይን አይቶ እስኪመለስ ድረስ ጥቂት ጥቂት ያደራርግ ነበር ።

በእንተ ጸዕሩ ወሞቱ ለኢየሱስ

፵፭ ወእምስሱ ሰዓት ጸልመ ኵሉ ዓለም እስከ ተሱዓት ሰዓት ፤

፵፭ ከቀትር እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ጨለማ ሆነ ።

፵፮ ወጊዜ ተሱዓት ሰዓት ጸርሐ እግዚእ ኢየሱስ በቃል ዓቢይ ። መዝ ፳፩ ፡ ፩
፵፮ በዘጠኝ ሰዓት ጊዜም ጌታ እሰምቶ ተናገረ ፤ እንዘ ይብል ኤሎሄ ኤሎሄ ኤልማስ ለማ ሰበቅታኒ ዝውእቱ ብሂል አምላኪየ አምላኪየ ለምንት ኀደገኒ፤ ኤሎሄ ኤሎሄ ያለውን አምላኪየ አለው ኤልማስ ያለውን ለምንትኑ አለው ሰበቅታኒ ያለውን ኀደገኒ ብሎ ተረጐመው አምላኪየ አዎ ላኪየ ለምንት ተዉከኝ እለ ኃደገ ብየ ሲል በኀዱጋኑ ተገብቶ ይጸልያል ።
፵፯ ወሰሚዖሙ እለ ይቀውሙ ይቤሉ ኤልያ ስሃ ይጼውዕ ዝሰ ።
፵፯ ከዚያ ቁመው ያሉት ኤሎሄ ኤሎሄ ሲል ሰምተው ይህስ ኤልያስን ይጠራል አሉ ።

፵፰ ወውእተ ጊዜ ሮጸ ፩ እምኔሆሙ ወነሥአ ሰፍነገ ወመልአ ብሒአ ወአሰረ ውስተ ሀለት ወአዕ አዘዞ ውስተ አፉሁ ወአስተዮ ።

፵፰ ያን ጊዜ ከሳቸው አንዱ ፈጥኖ ሰፍነግ ወሰደ መጣጣውን መልቶ በዘንግ አስሮ አጠጣው ሐተታ፤ሰፍነግ የጁህ ባዘቶ እንደ ዓይነ በጐ ያለ ውኃ የሚያነግ ቤት የሚጠርጉበት ነው ።

፵፱ ወቦ እለ ይቤሉ ኅድጉ ንርአይ ለእመ ይመጽእ ኤልያስ ያድኅኖ ።

፵፱ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደሆነ ተውት እንይ ያሉ አሉ ።

፶ ወጸርሐ እግዚእ ኢየሱስ በዓቢይ ቃል ።
፶ ጌታ አሰምቶ ተናገረ ።
ወመጠወ ነፍሶ ወወፅአት መንፈሱ ሶቤሃ ፤
ቅድስት ነፍሱ ከሥጋው ተለየች ።
ወመጽአ ፩ ወነሥአ ኲናተ ወረገዞ ገቦሁ ወውኅዘ ደም ወማይ ።
ቆመው ካሉት አንድ ሰው ጦሩን አንሥቶ ጎኑን ወጋው ወኃና ደም ሳይቀላቀል ፈሰሰ ።

፶፩ ወተሠጠ መንጦላዕተ ቤተ መቅደስ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ ፪ ኅጹጸን ፫፡ ፲፱ ።
፶፩ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ ።
ወኮነ ፪ኤ ክፍለ ።
ከሁለት ተከፈለ ።
ወመጽአ መልአክ ኀሩይ እማእከለ ኲሎሙ መላእክት እንዘ ይእኀዝ በእዴሁ ሰይፎ ክሡተ ከመ ያጥፍዖሙ ለዓላውያን ፍጡነ ወሰበ ከልዓቶ ምሕረቱ ለክርስቶስ ዘበጠ ዝኩ መልአክ በሰይፉ ለመንጦላዕተ ምኵራብ ወሠጠጦ ወረሰዮ ፪ተ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ እንዲል ኖራውን ስነጠቀው ፤ አንድም አንዱን ዘሀ ከሁለት አደረገው ።
አድለቅለቀት ምድር ።
ምድር ተናወጠ መርገመ ሥጋ ጠፋ ።
ወነቅዓ ኰኵሕ ።
እዕባን ተፈተቱ መርገመ ነፍስ ጠፋ ።
፶፪ ወተከሥቱ መቃብራት ።
፶፪ መቃብራት ተከፈቱ ሙስና መቃብር ጠፋ ።
ወተንሥኡ ብዙኃን አብድንቲሆሙ ለጻድቃን ።
የብዙ ጻድቃን በድን ማለት አምስት መቶ ሙታን ከመስቀል እግር ተነሡ ።
፶፫ ወቦኡ ውስተ ሀገር ቅድስት እምድኅረ ተንሥአ ።
፶፫ ከተነሣም በኋላ ወደቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ ።
ወአስተርአይዎሙ ለብዙኃን ።
ለብዙ ሰዎች ታዩዋቸው አለ ለዘመዶቻቸው ሦስቱን ቀን ወዴት ኑረው ቢሉ በደብረ ዘይት ።

፶፬ ወመኰንንሰ ፻ሰ ወእለ ምስሌሁ የዓቅብዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ርእዮሙ ውእተ ድልቅልቀ ፈርሁ ጥቀ ።
፶፬ የመቶ አዝማች ከሱም ጋራ ጌታን ሲጠብቁት የዋሉት መናወጡን ማለት የተደረገውን ተአምራት ባዩ ጊዜ ፈጽመው ፈሩ ።
ወይቤሉ እሙን ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ ።
በውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነው ።
፶፭ ወሀለዋ ህየ ብዙኃት አንስት እለ ይሬእያ እምርኁቅ ኲሎ ዘኮነ
፶፭ ከዚያም የተደረገውን ሁሉ ርቀው የሚያዩ ብዙ ሴቶች ነበሩ ወውእቶን እለ ተለዋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ እምገሊላ ።
እሳቸውም ኢየሱስን ከገሊላ የተከተሉት ፤
እለ ይትለአካሁ ።
የሚያገለግሉት ናቸው ።
፶፮ ወእማንቱ ማርያም መግደላዊት ፤
፶፮ ብዙ ሴቶችም የተባሉ ማርያም መግደላዊ ናት መግደሎን ይባላል አገሯ ።
ወማርያም እመ ያዕቆብ ወእሙ ለዮሳ ፤
የዮሳና የያዕቆብ እናት ናት ።
ወእሞሙ ለደቂቀ ዘብዴዎስ ።
የዘብዴዎስ ልጆች እናት ማርያም ባውፍልያ ናት ።

ዘከመ ተቀብረ ኢየሱስ ።

፶፯ ወመስዮ መጽአ ብእሲ ባዕል እምአርማትያስ ዘስሙ ዮሴፍ ።
፶፯ ሲመሽ በመሸ ጊዜ ዮሴፍ የሚባል ባለጸጋ ሰው መጣ ።
ወውእቱ ይፀመዶ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ከጌታ ዘንድ ይማር ነበር ።
፶፰ ወሖረ ኀበ ጲላጦስ ወሰአለ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ
፶፰ ከጲላጦስ ሂዶ ፥ የጌታን ሥጋ ላውርድ ብሎ ለመነ ፤
ወአዘዘ ጲላጦስ የሀብዎ ።
ጲላጦስ ስጡት ብሎ አዘዘ ።
፶፱ ወነሢኦ ሥጋሁ ዮሴፍ ገነዞ በሰንዱናት ንጹሕ ።
፶፱ ዮሴፍ ሥጋውን አውርዶ በድርብ በፍታ ገነዘው ።
፷ ወቀበሮ ውስተ መቃብር ሐዲስ ዘሎቱ አውቀረ ውስተ ኰኵሕ ።
፷ ለራሱ ብሎ ባሳነጸው ባዲስ መቃብር ቀበረው ። ሐተታ እንግዳ ሥራ እሠራላችኋለሁ ሲል ። አንድም እንደ ኤልሳዕ ኀባሬ ተአምራት ነቢይ በተቀበረበት እንጂ ቢቀበር አስነሣው እንዳይሉ ።
ወአንከርከረ እብነ ዓቢየ ዲበ ኆኅተ መቃብር ወኃለፈ ።
ታላቅ ደንጊያ አገላብጦ መቃብሩን ገጥሞት ሄደ ።

፷፩ ወሀለዋ ሀየ ማርያም መግደላዊት ወካልዕታሂ ማርያ ይነብራ ኀበ መቃብር ።

፷፩ ማርያም መግደላዊት ማርያም ባውፍልያ ከመቃብሩ ፊት ለፊት ተቀምጠው ነበር ።

፷፪ ወበሳኒታ እንተ ይእቲ እምድኅረ ዓርብ ተጋብኡ ሊቃነ ካህናት ወፈሪሳውያን ኀበ ጲላጦስ ።
፷፪ ያችም ከዓርብ ቀጥላ ናት በነጋው ቅዳሜ ፈሪሳውያንና ሊቃነ ካህናት ወደጲላጦስ ተሰብስበው
፷፫ ወይቤልዎ ተዘከርነ እግዚኦ ዘይቤ ዝኩ መስሐቲ እመ ሕያው ውእቱ እመ ሣልስት ዕለት እትነሣእ ።

፷፫ ያመስሐቲ በሕይወተ ሥጋ ሳለ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ ያለውን እናውቃለንና ።
፷፬ አዝዝ እንከ ይዕቀቡ መቃብሪሁ እስከ ሠሉስ መዋዕል ከመ ኢይምጽኡ አርዳኢሁ ወኢይሰርቅዎ ሌሊተ ወኢይበሉ ለሕዝብ ተንሥአ እምነ ሙታን ።
፷፬ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ሌሊት ሰርቀው ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ብለው ለሕዝቡ እንዳያስተምሩ መቃብሩን እስከ ሦስት ቀን ይጠብቁ ዘንድ እዘዝ አሉት ።
ወትከውን ደኃሪተ ጌጋዩ እንተ ተአኪ እምቀዳሚት ።
የኋላ ስህተቱ ከቀደመው የጸና ይሆናል ።
፷፭ ወይቤሎሙ ጲላጦስ ንሥኡ ሠገራተ ሑሩ ወአጽንዑ መቃብሪሁ በከመ ተአምሩ ።
፷፭ ጲላጦስም ጭፍራ ወሰዳችሁ እንደምታውቁ አጽንታችሁ አስጠብቁ አላቸው ።
፷፮ ወሖሩ ወአጽንኡ ወቀተሩ መቃብሮ ።
፷፮ ሄደው አጽንተው መቃብሩን ቈለፉት ።
ወኃተምዋ ለይእቲ እብን ምስለ ሠገራት ።
ጭፍራውን ይዘው ቈለፉ ። ሐተታ በህልቀቱ ወበህልቀተ መገብቱ እንዲል ተጠራጥረዋል እሱ እሳቸውን ጠርጥሯቸዋልና በማተሚያው ያትማል እሳቸው እሱን ጠርጥረውታልና በማተሚያቸው ያትማሉ ።

በእንተ ትንሣኤሁ ለኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፳፰ ።

፩ ወሠርከ ሰንበት ለጸቢሐ እሑድ መጽአት ማርያም መግደላዊት ወካልዕታኒ ማርያም ይርአያ መቃብረ ። ማር ፲፮ ፥ ፩ ዮሐ ፳ ፥ ፲፩ ።
፩ ቅዳሜ ማታ ለእሑድ አጥቢያ ማርያም መግደላዊት ሌላይቱም ማርያም መቃብሩን ያዩ ዘንድ መጡ ማርያም ባውፍልያ ናት ።
፪ ወናሁ ኮነ ድልቅልቅ ዓቢይ ።
፪ ታላቅ ንውጽውጽታ ተደረገ ።
እስመ መልአከ እግዚአብሔር ወረደ እምሰማይ ወቀርበ ወአንኰርኰራ ለይእቲ እብን እምአፈ መቃብር ወነበረ ዲቤሃ ።
መልአኩ ከሰማይ ወርዶ ደንጊውን ከመቃብር ላይ አንስቶ ተቀምጦበት ነበርና ።

፫ ወራእዩ ከመ ዘመብረቅ ።
፫ መልኩ እንደ ፀሐይ ብሩህ ነው ኢትርአይ ግርማ ርእየቱ ለኤልያብ እንዲል ።
ወልብሱ ፀዓዳ ከመ በረድ ።
ልብሱ እንደ በረዶ ነጭ ነው ወርኃ ትፍሥሕት ወርኃ ተድላ ነው ሲል ።

፬ ወእምግርማሁ ተሀውኩ እለ የዓቅቡ መቃብረ ወኮኑ ከመ አብድንት ።

፬ እሱን ከመፍራታቸው የተነሣ መቃብሩን የሚጠብቁት ደንግጠው እንደ በድን ሆኑ ። ሐተታ ፤ ነፍስ አልተለያቸውምና ከመ ዓብድንት አለ ።

፭ ወአውሥአ ውእቱ መልአክ ወይቤሎን ለአንስት እለ ይቀውማ ኢትፍርሃ አንትንሰ ።
፭ መልአኩ ሴቶችን እናንተ አትፍሩ አላቸው እስመ አአምር ከመ ኢየሱስሃ ዘተሰቅለ ተኃሥሣ ።
የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ ዐውቃለሁና ።
፮ ኢሀሎ ዝየሰ ።
፮ ከዚህ ግን የለም ።
ዳዕሙ ተንሥአ በከመ ይቤ ።
እነሣለሁ እንዳለ ተነሥቷል እንጂ ።
ወባሕቱ ነዓ ርእያ መካኖ ኀበ ተቀብረ ።
ነገር ግን የተቀበረበትን ቦታ መጥታችሁ እዩ ።
፯ ወፍጡነ ሑራ ወንግራሆሙ ለአርዳኢሁ ከመ ተንሥአ እምነ ምውታን ።
፯ ፈጥናችሁ ሄዳችሁ ከሙታን ተለይቶ እንደ ተነሣ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሯቸው ።
ወናሁ ይቀድመክሙ ገሊላ ።
በገሊላ ይቀድማችኋል ማለት መታየትን በገሊላ ይጀምርላችኋል ፤
ወበህየ ትሬእይዎ ።
በገሊላ ታዩታላችሁ ።
ናሁ አይዳዕኩክን ።
እነሆ ነገርኋችሁ ።
፰ ወኃለፋ ፍጡነ እልኩ አንስት እምኀበ መቃብር በፍርሃት ወበረዓድ ወበፍሥሐ ዓቢይ ።
፰ በታላቅ ደስታና በፍርሃት ከመቃብሩ ፈጥነው ሄዱ ። ሐተታ መልአክ አይተዋልና በፍርሃት ትንሣኤውን ሰምተዋልና ደስ ብሏቸው ሄዱ ።
ወሮጻ ይንግራሆሙ ለአርዳኢሁ ።
ለደቀ መዛሙርቱ ሊነግሯቸው ፈጥነው ሄዱ ።
፱ ወእንዘ የሐውራ ይንግራሆሙ ተራከቦን እግዚእ ኢየሱስ በፍኖት ።
፱ ሊነግሯቸው ሲሄዱ ጌታ ከመንገድ ታያቸው ወይቤሎን በሀከን ፤
እንዴት ሰነበታችሁ አስታረቅኋችሁ አላቸው ።

ወቀሪቦን ወአኃዛ እገሪሁ ወሰገዳ ሎቱ ።
ቀርበው እግሩን ይዘው እጅ ነሥት ሰገዱለት ።

፲ ወእምዝ ይቤሎን እግዚእ ኢየሱስ ኢትፍርሃ
፲ ከዚህ በኋላ ጌታ አትፍሩ አላቸው ።
ሑራ ንግራሆሙ ለአኃውየ ከመ ይሑሩ ገሊላ ፤
ገሊላ ይሄዱ ዘንድ ለወንድሞቼ ሄዳችሁ ንገሯቸው፤
በወህየ ይሬእዩኒ ፤
በገሊላ ያዩኛል ፤

ዘከመ ጌጥዎሙ ።

፲፩ ወኃሊፎን እማንቱ አተው ሠገራት ሀገረ ወነገሩ ለሊቃነ ካህናት ኵሎ ዘከመ ኮነ ።

፲፩ ሴቶች ከሄዱ በኋላ ጭፍሮች ከከተማ ገብተው የተደረገውን ሁሉ እንደተደረገ ለሊቃነ ካህናት ተናገሩ ።

፲፪ ወተጋብኡ ወተማከሩ ምስለ ሊቃውንት ወወሀብዎሙ ብዙኃ ወርቀ ለሠገራት ።

፲፪ ተሰብስበው ካለቆች ጋራ መክረው ለጭፍሮች ብዙ ወርቅ ሰጧቸው ።

፲፫ ወይቤልዎሙ በሉ አርዳኢሁ ሌሊተ መጽኡ ወሰረቅዎ እንዘ ንነውም ንሕነ ።
፲፫ እኛ ተኝተን ሳለን ሌሊት መጥተው ደቀ መዛሙርቱ ሰርቀው ወሰዱት በሉ አሏቸው ።
፲፬ ወእምከመ ተሰምዓ ዝነገር በኀበ መልአከ አሕዛብ ንሕነ ነአምኖ ።
፲፬ ይህ ነገር በጲላጦስ ዘንድ የተሰማ እንደሆነ እኛ እናስረዳዋለን ።
ወለክሙሰ ናድኅነክሙ ።
እናንተንም ከቅጣት እናድናችኋለን ።
ወናጸድቅ ነገረክሙ ነገራችሁንም እናስረዳለን ።
ወዘእንበለ ኃዘን ንሬስየክሙ ።
ደስ እናሰኛችኋለን አሏቸው ።
፲፭ ወነሚአሙ ሠገራት ውእተ ወርቀ ገብሩ በከመ መሐርዎሙ ።
፲፭ ጭፍሮች ገንዘቡን ተቀብለው እንደነገሯቸው አደረጉ ማለት ሰርቀው ወሰዱት አሉ ።
ወወፅአ ዝንቱ ነገር በኀበ አይሁድ እስከ ዮም ።
እስካሁን ድረስ በአይሁድ ዘንድ ሰርቀው ወሰዱት ፤ ተብሎ ሲነገር ይኖራል ። ሐተታ አለቆቻቸው አራት ናቸው እየራሳቸው ጠይቀዋቸዋል አንዱን ቢጠይቁት ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርቱ ሰርቀው ወሰዱት አለ ። አንዱ መቶ ሃያው ቤተ ሰቡ ሰርቀው ወሰዱት አለ ፡ አንዱ ፤ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ሰርቀው ወሰዱት አለ ። አንዱን ፡ እኔ ተኝቼ ነበር ሁሉንም አላየሁም አለ ፤ ከመዝኑ ኮነ ነገርክሙ ዝርዙረ ወዝርው ብሎ በሰይፍ አስፈጅቷቸዋል ።
፲፮ ወአርዳኢሁሰ ፲ቱ ወ፩ዱ ሖሩ ውስተ ገሊላ ኀበ ደብር ዘአዘዞሙ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፮ ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርቱ ግን ሂዱ ወዳላቸው ቦታ ወደገሊላ ሄዱ ።

፲፯ ወሶበ ርእይዎ ሰገዱ ሎቱ ።
፲፯ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት ።
ወመንፈቆሙሰ ናፈቁ ።
እኩሌቶቹ ተጠራጠሩ አለ ቶማስን ሲያይ ፤ ወንፍቃ ለሌሊት እንዲል ።

፲፰ ወቀርበ እግዚእ ኢየሱስ ወተናገሮሙ እንዘ ይብል ተውህበኒ ሥልጣን ሰማይ ወምድር ።

፲፰ ጌታ ቀርቦ ሰማይን ምድርን የማሳልፍበት ሥልጣን ተሰጠኝ ብሎ ነገራቸው ። ሐተታ ነፍሱና ሥጋው ተለያይተው ነበርና የኒያን ተዋሕዶ ሲያይ ተውህበ ሊተ አለ አንጂ የተሰጠው በማኅፀን ሲዋሐድ ነው ።
በከመ ፈነወኒ አቡየ እነኒ እፌንወክሙ ።
እኔን አባቴ ላስተምር እንደላከኝ እናንተንም እልካችኋለሁ ።

፲፱ ሑሩ ወመሐሩ ኵሎ አሕዛበ ። ማር፡፲፮፡፲፭ ።
፲፱ ሄዳችሁ ሰውን ሁሉ አስተምሩ ። ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ።
ስታጠምቋቸውም በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብላችሁ አጥምቋቸው ።

፳ ወመሐርዎሙ ኵሎ ይዕቀቡ ኵሎ ዘአዘዝኩክሙ ።
፳ መሐርዎሙ ዘአዘዝኩክሙ ይዕቀቡ ዘአዘዝኩክሙ ብለህ ግጠም ያዘዝኋችሁን ሁሉ አስተምሯቸው ።
ወናሁ አነ እሄሉ ምስሌክሙ በኵሉ መዋዕል እስከ ኅልፈተ ዓለም ።
እኔም እነሆ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ባላችሁበት ዘመን አድሬባችሁ እኖራለሁ በሐዋርያት መላውን መናገር ነው ።
መልአ ጽሕፈት ብሥራቱ ለማቴዎስ ሐዋርያ ፩ዱ እም፲ወ፪ቱ ሐዋርያት ።
ካሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ማቴዎስ የጻፈው ወንጌል ደረሰ ተፈጸመ ።
ወኮነ ጸሐፎ በፍልስጥዔም በአስተሐምሞ መንፈስ ቅዱስ እምድኅረ ዕርገቱ ለእግዚእነ ውስተ ሰማይ ዘበእጾርግዮ በሰማኒት ዓመት ።
ጌታ በሥጋ ወደሰማይ ካረገ በኋላ በስምንተኛው ዓመት መንፈስ ቅዱስ እያተጋው በፍልስጥዔም የጻፈው ።
ወበቀዳሚት ዓመተ መንግሥቱ ለቀላውዴዎስ ቄሣር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ።
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ፡ አስተምሮ ላስጨረሰን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን ።

ኍልቈ ምዕራፍ ዓቢይ ዘወንጌለ ማቴዎስ ።	የማቴዎስ ወንጌል ዓቢይ ምዕራፍ ቍጥር ።
ምዕራፍ ፩ መጽሐፈ ልደቱ ።	የልደቱ መጽሐፍ ።
ም ፪ ወተወሊዶ ።	በተወሰደ ጊዜ ።
ም ፫ ወበውእቱ መዋዕል ።	በዚያ ወራት ።
ም ፬ ወእምዝ ወሰዶ መንፈስ ።	ከዚህ በኋላ ወሰደው ።
ም ፭ ወርእዮ አሕዛበ ።	ብዙ ሰው አይቶ ።
ም ፮ ወባሕቱ ዑቁ ።	ነገር ግን ዕወቁ ።
ም ፯ ኢትኰንኑ ።	አትፍረዱ ።
ም ፰ ወእንዘ ይወርድ እምደብር ።	ከተራራ ሲወርድ ።
ም ፱ ወዐሪጎ ውስተ ሐመር ።	ከመርከብ በወጣ ጊዜ ።
ም ፲ ወጸውዖሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ።	ዐሥራ ሁለቱን ጠራ ።
ም ፲፩ ወኮነ ድኅረ ፈጸመ ።	አስተምሮ ከጨረሰ በኋላ ።
ም ፲፪ ወበውእቱ መዋዕል ።	በዚያ ወራት ።
ም ፲፫ ወበይእቲ ዕለት ወፂአ ።	በዚያች ቀን ከቤት ወጥቶ ።
ም ፲፬ ወበውእቱ መዋዕል ሰምዓ ሄሮድስ ።	በዚያ ወራት ሄሮድስ ሰማ ።
ም ፲፭ ወእምዝ ቀርቡ ኀበ ኢየሱስ ።	ወደ ጌታ ቀረቡ ።
ም ፲፮ ወመጽኡ ፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን ።	ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን መጡ ።
ም ፲፯ ወእምድኅረ ሰሱ መዋዕል ።	ከስድስት ቀን በኋላ ።
ም ፲፰ ወበይእቲ ሰዓት ።	በዚያች ሰዓት ፤
ም ፲፱ ወኮነ እምዘፈጸመ ኢየሱስ ።	አስተምሮ ከጨረሰ በኋላ ፤
ም ፳ እስመ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ።	መንግሥተ ሰማያት ባለቤትን ትመስላለች ።
ም ፳፩ ወቀሪቦ ኢየሩሳሌም ።	ወደ ኢየሩሳሌም በቀረበ ጊዜ ።
ም ፳፪ ወአውሥአ ኢየሱስ ዳግመ ።	ጌታ ዳግመኛ መለሰ ፤
ም ፳፫ ወእምዝ ነገሮሙ ኢየሱስ ለሕዝብ ።	ጌታ ለሕዝቡ ነገራቸው ፤
ም ፳፬ ወወፂአ እምቤተ መቅደስ ።	ከቤተ መቅደስ በወጣ ጊዜ ፤
ም ፳፭ አሜሃ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ።	ያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት ሙሽራን ትመስላለች።
ም ፳፮ ወኮነ እምዘፈጸመ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ።	አስተምሮ ከጨረሰ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው
ም ፳፯ ወጸቢሖ ተማከሩ ።	ሲነጋ ሊገድሉት መከሩ ።
ም ፳፰ ወሰርከ ሰንበት ።	ቅዳሜ ማታ ።

* * *

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ማቴዎስ ።			የማቴዎስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ መጽሐፈ ትውልድ ዘኢየሱስ ክርስቶስ ።	ምዕራፍ ፩	ቍጥር ፩	የኢየሱስ ክርስቶስን የትውልዱን ታሪክና ቍጥር ስለ መንገር ።
በእንተ ልደተ ክርስቶስ ።		ቍ ፲፰	ስለ ጌታ መወለድ ።
ዘከመ መጽኡ ሰብአ ሰገል ውስተ ቤተ ልሔም ።	ም ፪	ቍ ፩	ሰብአ ሰገል ወደ ቤተ ልሔም እንደ መጡ ስለመንገር ።
ዘከመ ጐየ ውስተ ግብጽ ።		ቍ ፲፫	ወደ ግብጽ እንደ ሄደ ።
በእንተ ቅትለት ዘሕፃናት ።		ቍ ፲፮	ስለ ሕፃናት መሞት ።
በእንተ ሚጠት እምነ ግብጽ ።		ቍ ፲፱	ከግብጽ ስለ መመለስ ።
በእንተ ስብከት ዘዮሐንስ መጥምቅ ።	ም ፫	ቍ ፩	ስለ ዮሐንስ መጥምቅ ማስተማር ።
በእንተ ጥምቀት ዘኢየሱስ		ቍ ፲፫	ስለ ጌታ መጠመቅ ።
በእንተ ተመከሮት ዘኢየሱስ	ም ፬	ቍ ፩	ስለ ጌታ መፈተን ።
ዘከመ ነበረ ኢየሱስ በቅፍርናሆም ።		ቍ ፲፪	ጌታ በቅፍርናሆም እንደ ተቀመጠ ።
በእንተ አርባዕቱ ቀዳማውያን ሐዋርያት ።		ቍ ፲፰	ስለ አራቱ ሐዋርያት መመረጥ ።
በእንተ ቀዳማዊ ስብከት ወመንክራቲ ለኢየሱስ።		ቍ ፳፫	ጌታ መጀመሪያ ስለ አስተማረውና ስለ አደረገው ተአምራቱ ።
ዘከመ ሰበከ መልዕልተ ደብር በእንተ ብፁዓን	ም ፭	ቍ ፩	ስለ ብፁዓን በተራራ ላይ እንዳስተማረ ።
በእንተ ሐዲስ ኪዳን ተአርዮታ ምስለ ብሊት ።		ቍ ፲፯	ብሉይና ሐዲስን ስለ ማስተካከል ።
በእንተ ንጽሕት ሕሊና ወውሂበ ምጽዋት ወበእንተ ጾም ወጸሎት ።	ም ፮	ቍ ፩	ምጽዋትን በመስጠት በጾም በጸሎት ልብን ስለ ማንጻት ።
በእንተ ዘይደልዎሙ ለክርስቲያን ወበእንተ ንዋየ ዓለም ።		ቍ ፲፱	ለክርስቲያን ስለሚገባቸው ነገርና ስለ ዓለም ገንዘብ
በእንተ ትእዛዛት ።	ም ፯	ቍ ፩	ስለ ትእዛዛት ።
በእንተ አድኅኖተ ለምጻዊ ።	ም ፰	ቍ ፩	ለምጽ የታመመውን ስለ ማዳን ።
በእንተ ገብረ መስፍን ።		ቍ ፭	ስለ ሹም ባሪያ ።
በእንተ ሐማተ ጴጥሮስ ።		ቍ ፲፬	ስለ ጴጥሮስ አማት ።
በእንተ ዘከመ ይደሉ ተሊዎተ ኢየሱስ		ቍ ፲፰	ጌታን መከተል እንዲገባ ።
በእንተ ዘከመ እኅድአ ለባሕር		ቍ ፳፫	ባሕርን ጸጥ እንዳደረገ ።
በእንተ አጋንንት ዘብሔረ ጌርጌሴኖን	ም ፰	ቍ ፳፰	በጌርጌሴኖን ስለ ነበሩ አጋንንት ።
በእንተ መጻጉዕ	ም ፱	ቍ ፩	መፃጉዕን እንደ አዳነ ።
በእንተ ዘከመ ተጸውዐ ማቴዎስ ።		ቍ ፱	ማቴዎስ እንደ ተመረጠ ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎሙ ለክርስቲያን ጾዊመ ።		ቍ ፲	ለክርስቲያን መጾም እንዲገባ ።
በእንተ ወለተ ኢያኤሮስ ወበእንተ ደም ዘይውኅዝ		ቍ ፲፰	የኢያኢሮስን ልጅና ደሟ የሚፈስን ስለ አዳነ ።
በእንተ ፪ቱ ዕውራን ።		ቍ ፳፯	ሁለት ዕውሮች እንደ ተከተሉት ።
በእንተ ጽሙም ዘቦቱ ጋኔን ።		ቍ ፴፪	ደንቆሮ ጋኔን ስለ አደረበት ።
በእንተ ዘከመ አንሶሰወ ኢየሱስ ውስተ ገሊላ ።		ቍ ፴፭	ጌታ በገሊላ ዞሮ ስለ አስተማረ ።
በእንተ ዘከመ ተፈነዉ ሐዋርያት ።	ም ፲	ቍ ፪	ሐዋርያት እንደ ተላኩ ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ማቴዎስ ።		የማቴዎስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ዘከመ መሐሮሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት ።	ቍ ፭	ጌታ ሐዋርያትን እንዳስተማረ ።
በእንተ ኢየሱስ ወአርዳኢሁ ለዮሐንስ መጥምቅ ።	ም ፲፩ ቍ ፪	ስለ ጌታና ስለ ዮሐንስ ተማሪዎች ።
በእንተ ዘከመ ወደሶ ኢየሱስ ለዮሐንስ መጥምቅ ።	ቍ ፯	ጌታ ዮሐንስን እንደ አመሰገነው ።
በእንተ ዘከመ ኄሰን ለአኅጉር ኢንሳሕያት ።	ቍ ፳	ያላመኑትን እንደ ነቀፋቸው ።
በእንተ ድኅነት ።	ቍ ፳፭	ስለ ማዳን ።
በእንተ ሰንበት ወሰዊት	ም ፲፪ ቍ ፩	ስለ ቅዳሜና ስለ እሸት ።
በእንተ ዘየብሰት እዴሁ ።	ቍ ፲	እጁ ስለ ደረቀች ።
በእንተ ርኅራኄሁ ለኢየሱስ ።	ቍ ፲፭	ስለ ጌታ ለሰው ማዘን ።
በእንተ ዕውር ወጽሙም ዘቦቱ ጋኔን ።	ቍ ፳፪	ስለ ዕውርና ደንቆሮ ጋኔን ያደረበት ።
በእንተ ጽልሑት ዘፈሪሳውያን ፡	ቍ ፴፩	ስለ ፈሪሳውያን ተንኮል ።
በእንተ ትእምርተ ዮናስ ።	ቍ ፴፰	ስለ ዮናስ ምልክት ።
በእንተ መናፍስት ርኩሳን ።	ቍ ፵፫	ስለ ክፉዎች አጋንንት ፥
በእንተ ሰብአ ቤቱ ለእግዚእ ኢየሱስ ።	ቍ ፵፮	ስለ ጌታ ቤተ ሰብ ፥
በእንተ ምሳሌ ዘራኢ ።	ም ፲፫ ቍ ፩	ስለ ገበሬ ዘር ምሳሌ ፥
በአንተ ምሳሌ ዘሥርናይ ሠናይ ወዘክርዳድ ።	ቍ ፳፬	ስለ በጎ ሥንዴና ስለ ክርዳድ ምሳሌ ፥
በእንተ ምሳሌ ዘሕጠተ ሰናፔ ።	ቍ ፴፩	ስለ ሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ ።
በእንተ ምሳሌ ዘብሑእ ።	ቍ ፴፫	ስለ እርሾ ምሳሌ ።
በእንተ ፍካሬ ዘምሳሌ ክርዳድ ።	ቍ ፴፮	የእንክርዳድ ምሳሌን ስለ መተርጐም ፥
በእንተ መድፍን ወባሕርይ ወገሪፍ ።	ምዕራፍ ፲፫ ቍጥር ፵፬	ስለ ተቀበረ ዕንቍና መረብ ።
በእንተ ዘከመ ሖረ ኢየሱስ ውስተ ናዝሬት ፡	ቍ ፶፫	ጌታ ወደናዝሬት እንደ ሄደ ፥
በእንተ ዘከመ ሐለየ ሄሮድስ ሳዕለ ኢየሱስ ።	ም ፲፬ ቍ ፩	ሄሮድስ በጌታ ላይ እንዳሰበ ።
በእንተ ምትረተ ዮሐንስ መጥምቅ ።	ቍ ፫	ስለ ዮሐንስ መቆረጥ ።
በእንተ ቀዳሚት አብዝኆተ ኅብስት ።	ቍ ፲፫	መጀመሪያ እንጀራ እንዳበረከተ ።
በእንተ ዘከመ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ መልዕልተ ማይ	ቍ ፳፪	ጌታ በውኃ ላይ እንደ ሄደ ።
በእንተ ዘከመ ዐደወ ውስተ ጌንሴሬጥ ።	ቍ ፴፬	ወደ ጌንሴሬጥ እንዳሻገረ ።
በእንተ ፈሪሳውያን ወሥርዓቶሙ ።	ም ፲፭ ቍ ፩	ስለ ፈሪሳውያን ሥራት ፥
በእንተ ከነናዊት እም ።	ቍ ፳፩	ስለ ከነናዊት ሴት ።
በእንተ ዘከመ ተፈወሱ ካልዓን ሕሙማን ።	ቍ ፳፱	ሌሎች በሽተኞች እንደዳኑ ፤
በእንተ ካልዕት አብዝኆተ ኅብስት ።	ቍ ፴፪	ሁለተኛ እንጀራ ስለ አበረከት ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ማቴዎስ ።		የማቴዎስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ዘከመ ኀሠሡ ትእምርተ እምሰማይ ያርእዮሙ፤ ምዕ ፲፮	ቍ ፩	ምልክትን ከሰማይ ሊያሳያቸው እንደ ፈለጉ ።
በእንተ ብሑአ ፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን ።	ቍ ፮	ስለ ፈሪሳውያንና ስለ ሰዱቃውያን እርሾ ።
በእንተ ዘከመ ተአመነ ጴጥሮስ	ቍ ፲፫	ጴጥሮስ እንደ አመነ ።
በእንተ ዘከመ ተነበየ ኢየሱስ ሕማሞ ።	ቍ ፳፩	ጌታ መከራውን እንደ ተናገረ ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ኀዲገ ርእሱ በእንተ ክርስቶስ ።	ቍ ፳፬	ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ራሱን መጣል እንዲገባው።
በእንተ ዘከመ ተወለጠ ገጹ ለኢየሱስ በደብረ ታቦር ምዕ ፲፯	ቍ ፩	በደብረ ታቦር የጌታ መልኩ እንደ ተለወጠ ፣
በእንተ ወርኃዊ ዘይጼአር	ቍ ፲፬	በጨረቃ ጊዜ ስለ ሚታመም ፣
በእንተ ውሂበ ጸባሕት ለቤተ መቅደስ ፡	ቍ ፳፬	ለቤተ መቅደስ ግብር ስለ መስጠት ፤
በእንተ ክርስቲያናዊት ትሕትና ምዕ ፲፰	ቍ ፩	ስለ ክርስቲያን ሰው ትሕትና ፤
በእንተ ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ በሳዕለ ዕቅፍት	ቍ ፯	ጌታ ሰውን ማሰናከል እንዳይገባ ስለ ተናገረ ፤
በእንተ በግዕት ዘተኀጕለት ፣	ቍ ፲፪	ስለ ጠፋች በግ ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎሙ ለእኁው ተገሥጾ ። ምዕራፍ ፲፰	ቍጥር ፲፭	ወንድሞችን መምከር እንዲገባ ፣
በእንተ ማህል ዘክርስቲያን ።	ቍ ፳፩	ስለ ክርስቲያን ይቅርታ ።
በእንተ ምሳሌ እግብርት ወፈድዮተ ዕዳ ፤	ቍ ፳፫	ስለ ባሮች ምሳሌና ዕዳን ስለ መክፈል ።
በእንተ ዘከመ ተግህሠ ኢየሱስ እምኢየሩሳሌም ። ምዕ ፲፱	ቍ ፩	ጌታ ከኢየሩሳሌም እንደ ሄደ ።
በእንተ ኪዳን ዘኢይትፈታሕ	ቍ ፫	ስለማይፈታ መሐላ ።
በእንተ ሕፃናት እለ መጽኡ ኀበ ኢየሱስ ።	ቍ ፲፫	ወደ ጌታ ስለ መጡ ልጆች ።
በእንተ ወሬዛ ባዕል ።	ቍ ፲፮	ስለ ባለጠጋ ጕልማሳ ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎሙ ዕሤተ ለእለ ይትልውዎ ።	ቍ ፳፯	ጌታን የሚከተሉ ዋጋ እንዲገባቸው ።
በእንተ ምሳሌ ዘዓቀብተ ወይን ምዕ ፳	ቍ ፩	ስለ ወይን ጠባቂዎች ምሳሌ ።
በእንተ ትንቢት ሣልሲት ዘሕማማት	ቍ ፲፯	ጌታ መከራውን ሦስተኛ እንደ ተናገረ ።
በእንተ ደቂቀ ዘብዴዎስ ።	ቍ ፳	ስለ ዘብዴዎስ ልጆች ።
በእንተ ዕውራን ዘኢያሪሆ	ቍ ፴	ኢያሪኮ ስለ አሉ ዕውሮች ።
በእንተ ዘከመ ቦአ እግዚእ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ። ምዕ ፳፩	ቍ ፩	ጌታ ኢየሩሳሌም እንደገባ ።
በእንተ ዘከመ ሰደዶሙ ኢየሱስ ለእለ ያረኵሱ ቤተ መቅደስ ።	ቍ ፲፪	ቤተ መቅደስ የሚያረክሱ አይሁድን ጌታ እንዳ ሰደዳቸው ።
በእንተ በለስ ዘተረግመት ።	ቍ ፲፰	ስለ ተረገመች በለስ ።
በእንተ ትውክልት ኀበ እግዚአብሔር ።	ቍ ፳	እግዚአብሔርን ስለ ማመን ።
በእንተ ዘከመ ተሰአሎሙ ለአይሁድ በእንተ ጥምቀተ ዮሐንስ ።	ቍ ፳፫	ጌታ አይሁድን ስለ ዮሐንስ ማጥመቅ እንደ ጠየቃቸው ።
በእንተ ፪ቱ ደቂቅ ።	ቍ ፳፰	ስለ ሁለቱ ልጆች ምሳሌ ።
በእንተ እኩያን ገባእተ ዐጸደ ወይን ።	ቍ ፴፫	ስለ ክፉዎች ወይን ጠባቆች ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ማቴዎስ ።		የማቴዎስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ምሳሌ ንጉሥ ዘገብረ ከብካበ ለወልዱ ፡	ም ፳፪ ቍ ፩	ስልጁ ሠርግ ስለ አደረገ ንጉሥ ምሳሌ ።
በእንተ ዘከመ ይደሉ ውሂበ ጸባሕት ለቄሣር ።	ቍ ፲፭	ለቄሣር ግብር መስጠት እንዲገባ ።
በእንተ ሰዱቃውያን ወትንሣኤ ሙታን ።	ቍ ፳፫	ስለ ሰዱቃውያንና ስለ ትንሣኤ ሙታን ።
በእንተ ዓቢይ ትእዛዝ እግዚአብሔር ።	ቍ ፴፬	ለስ እግዚአብሔር ትእዛዝ ።
በእንተ መሢሕ ወልደ ዳዊት ምዕራፍ ፳፪፡	ቍ፤ ፵፩	ስለ መሢሕ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ።
በእንተ መደልዋን ፈሪሳውያን	ም ፳፫ ቍ ፩	ስለ ግብዞች ፈሪሳውያን ።
በእንተ እከየ ፈሪሳውያን ።	ቍ ፲፫	ስለ ፈሪሳውያን ክፋት ።
በእንተ ዘከመ ኄሳ ለኢየሩሳሌም	ቍ ፴፯	ኢየሩሳሌምን እንደ ነቀፋት ።
በእንተ ዘከመ አቅደመ ነጊረ ሙስናሃ ለቤተ መቅደስ ወለኢየሩሳሌም	ም ፳፬ ቍ ፩	የኢየሩሳሌምንና የቤተ መቅደስን ጥፋት እንደ ተናገረ
በእንተ ካልአዊት ምጽአት ዘወልደ ዕጓለ እመሕያው	ቍ ፳፱	ስለ ሁለተኛዪቱ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ መምጣት ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎ ተጊሀ ለክርስቲያን ።	ቍ ፵፪	ለክርስቲያን መትጋት እንዲገባው ።
በእንተ ፲ቱ ደናግል ጠባባት ወዓብዳት ።	ም ፳፭ ቍ ፩	ስለ ልባሞችና ስለ ሰነፎች ዐሥር ደናግል ።
በእንተ ምሳሌ መካልይ ።	ቍ ፲፬	ስለ ወርቅ ምሳሌ ።
በእንተ ኅልቀተ ዓለም	ቍ ፴፩	ስለ ዓለም ማለፍ ።
ዘከመ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት በሳዕለ ኢየሱስ	ም ፳፮ ቍ ፫	የካህናት አለቆች በጌታ ላይ እንደ መከሩ ።
በእንተ ዘከመ ረፈቀ ኢየሱስ ለድራር በቢታንያ ወተካይዶቱ ለይሁዳ	ቍ ፮	ጌታ በቢታንያ ለራት እንደ ተቀመጠ ይሁዳም ከሊቃነ ካህናት ጋራ እንደ ተማማለ ።
በእንተ ደኃሪት ድራር ወእስተዳልዎ ።	ቍ ፲፯	ስለ ሁለተኛዪቱ ራት መዘጋጀት ።
በእንተ ዘከመ ከሠተ ኢየሱስ ለዘያገብዖ ።	ቍ ፳	የሚያሲዘውን ጌታ እንደ ገለጠ ።
በእንተ ዘከመ ሠርዓ ኢየሱስ አኰቴተ ቍርባን ።	ቍ ፳፮	ጌታ ቍርባንን እንደሠራ ።
በእንተ አቅደመ ኢየሱስ ነጊረ ዕልወተ አርዳኢሁ ፡	ቍ ፴	ጌታ የተማሪዎቹን ክህደት አስቀድሞ እንደ ተናገረ።
በእንተ ዘከመ ጸለየ ኢየሱስ በጌቴሴማን ።	ቍ ፴፮	ጌታ በጌቴሴማን እንደጸለየ ።
በእንተ ዘከመ አግብአ ይሁዳ ለክርስቶስ ወዘከመ ተእኅዘ	ቍ ፵፯	ይሁዳ ክርስቶስን እንደ አስያዘው ክርስቶስም እንደ ተያዘ ።
በእንተ ዘከመ ቆመ ኢየሱስ በቅድመ ዓውድ ።	ቍ ፶፯	ጌታ ባደባባይ እንደ ቆመ ።
በእንት ክሀደተ ጴጥሮስ ።	ቍ ፷፱	ጴጥሮስ ጌታን እንደካደው ።
በእንተ ቀቢጸ ተስፋ ዘይሁዳ	ም ፳፯ ቍ ፫	ይሁዳ ተስፋ እንደቆረጠ ።
በእንተ ዘከመ ቆመ ኢየሱስ በቅድመ ጲላጦስ ።	ቍ ፲፩	ጌታ በጲላጦስ ፊት እንደቆመ ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ማቴዎስ ።		የማቴዎስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ዘከመ ኅረይዎ ለበርባን እምነ ኢየሱስ ወዘከመ ኰነንዎ	ቍ ፲፭	በርባንን ከጌታ ይልቅ እንደመረጡት በጌታም እንደ ፈረዱበት ።
ዘከመ ተሣለቁ ላዕለ ኢየሱስ ም ፳፯	ቍ ፳፯	በጌታ እንደ ዘበቱበት ።
በእንተ ፍኖተ መስቀል	ቍ ፴፪	ስለ መስቀል መንገድ ።
በእንተ ዘከመ ተሰቅለ ኢየሱስ	ቍ ፴፭	ጌታ እንደ ተሰቀለ ።
በእንተ ጻዕሩ ወሞቱ ለኢየሱስ	ቍ ፵፭	ስለ ጌታ ሞትና ጭንቀት ።
በእንተ ዘከመ ተቀብረ ኢየሱስ ።	ቍ ፶፯	ጌታ እንደ ተቀበረ ።
በእንተ ትንሣኤሁ ለኢየሱስ ም ፥ ፳፰	ቍ ፩	ጌታ እንደ ተነሣ ።
በእንተ ዘከመ ጌጥዎሙ ለዓቀብት	ቍ ፲፩	መቃብር ጠባቆችን እንዳ አባበሏቸው ።
በእንተ ዘከመ ተፈነዉ ሐዋርያት	ቍ ፲፮	ሐዋርያት እንደ ተላኩ ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል፤
ቅዱስ ማርቆስ እንደ ጻፈው ።

ብሥራተ ማርቆስ ረድኡ ፩ዱ እም፸ ወ፪ቱ አርድእት ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን ፤ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ማርቆስ ማለት ንህብ ማለት ነው ፤ ንህብ ከሁሉ እንዲቀስም አስቀድሞ ከክርስቶስ ኋላ ከሐዋርያት ተምሯልና ፤ አንበሳ ማለት ነው ። አንበሳ ለሳም ጌታው እንደሆነ እንዲሰብረው አምልኮተ ጣዖትን ከግብጽ አጥፍቷልና ፤ አንድም ክሆነ ልኡክ ማለት ነው ። ብሥራተ ማሪ ማርቆስ ይላል ቀተደ ረራዩ ቀለም ነው ሁሉም ካሆነ ማለት ነው እማል እዝቀ ሲናጺቀስ ባሉ ጊዜ መልእክትም ሲናጺቀስም ክታብ ማለት እንደሆነ ፤ ይህም ቃል የሠለስቱ ምዕት ነው እንደ ማቴዎስ ተርከ ። ይህን ዓለም ዕጣ በጣ ብለው ተካፍለው ለማስተማር በሚወጡበት ጊዜ ለቅዱስ ጴጥሮስ ሮም በዕጣ ደርሰዋለች እምስተኛ ግብጽን እንስቷል ። ይህስ አይደለም ብሎ ግብጽ በዕጣ ደረሰችው ። አምስተኛ ሮምን አንስቷል የንጉሡ ነገሥት መዲና ናትና ርሱም ሊቀ ሐዋርያት ነውና ፤

ለአርድእት ግን ዕጣ የላቸውም አንዱም ሁለቱም እየሆኑ አንዱን ሐዋርያ አንዱም ሁለቱም አንዱን ሐዋርያ ተከትለው ሄደዋል ። ማርቆስም ጴጥሮስን ተከትሎ ሄዷል ግብጽን ለማርቆስ ሰጥቶት እሱም ሮም ወርዷል።ማርቆስ ከዚህ ገብቶ ጌታ ከፅንስ ጀምሮ ያደረገውን ታምራት ያስተማረውን ትምህርት የሠራውን ትሩፋት ቢነግራቸው ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ተመለሱ አመኑ ተጠመቁ ።

ትምህርት ካልደረሰበት ለማዳረስ ወጥቶ በሚሄድበት ጊዜ አባታችን በቃል ያስ ይረሳል በመጽሐፍ ያስ ይወረሳልና ጻፍልን ብለው በዚያ ምክንያት ይጽፋል ።

አንድም እሱ እንዳባትነቱ ይጽፋል ። መዋዕለ ጽሕፈት ፤

ሐተታ፤እንደ ማቴዎስ ፡ ጸሐፍቱም ሁለቱ ከሐዋርያት ሁሉቱ ከአርድዕት ናቸው ሐዋርያት ጨርሰው እንዲጽፉት ያላደረገ ሁሉቱን ከአርድዕት ያጻፈ ስለምን ቢሉ ሐተታ ፡ እንደ ማቴዎስ አርድእት ጨርሰው እንዲጽፉት ያላደረገ ሁለቱን ከሐዋርያት ያጻፈ ስለምን ቢሉ ሐተታ፡እንደ ማቴዎስ ጸሐፍቱንስ ከፍ ብሎ አምስት ስድስት ዝቅ ብሎ ሁለት ሦስት ያላደረገ ስለምን ቢሉ ። ሐተታ እንደ ማቴዎስ ፤ ሀገርም ልሳንም ሐተታ እንደ ማቴዎስ ፤ ወንጌልሂ ብለህ እትት ይህን አርእስት። ሠለስቱ ምዕት ስጥተዋል ብለህ ጨርሰህ ተርከ ። ልመናው ክብሩ ይደርብንና ከሰባ ሁለቱ አርድዕት አንዱ ማርቆስ የጻፈው ወንጌል ይህ ነው ።

በእንተ ስብከተ ዮሐንስ ።

ምዕራፍ ፩ ።

፩ ቀዳሚሁ ለወንጌለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው በከመ ጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ ነቢያት ናሁ አነ እፌኑ መልአኪየ

፪ ቅድመ ገጽከ ዘይጼይሖ ፍኖተከ በቅድሜከ ቃለ ዓዋዲ ዘይሰብክ በገዳም ፤

፫ ወይብል ጺሑአ ፍኖተ እግዚአብሔር ወአርዩ መጽያሕቶ ። ኢሳ ፵ ፡ ፫ ። ማቴ ፫ ፡ ፫ ሉቃ ፫ ፡ ፬ ። ዮሐ ፩፡ ፳፫ ።

፩ ሕያው የሚሆን የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ፤ ፪ የወንጌል ጥንቱ ጥምቀተ ዮሐንስ ስብከተ ዮሐንስ ነው በከመ ጽሑፍ ውስተ መጻሕፍተ ነቢያት ። ሚክ ፡ ፫ ፡ ፩ ።

፫ በመጻሕፍተ ነቢያት እንደ ተነገረ ዘንድ ። አንድም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው የወንጌል ጥንቱ በመጻሕፍተ ነቢያት እንደ ተነገረ ዘንድ ነው ። አንድም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው የወንጌል ጥንቱ እምላክ ሰው እንደ ሆነ ዘንድ ነው ።

በከመ ጽሑፍ ።

በመጻሕፍተ ነቢያት እንደተነገረ ፡ እፌኑ ያለውን ይሻል ። አንድም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው የወንጌል ጥንቱ ሰው አምላክ እንደሆነ ዘንድ ነው ። መልአኪየ ያለውን ይሻል ። በከመ ጽሑፍ በመጻሕፍተ ነቢያት እንደተነገረ ዘንድ ። አንድም ቀዳሚሁ ለወንጌለ ኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል ጥንቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። በከመ ጽሑፍ በመጻሕፍተ ነቢያት እንደተነገረ ዘንድ ። ሐተታ መጻሕፍተ ነቢያት ያለ እንደ ሆን አያሳስትም መጽሐፈ ነቢይ ያለ እንደሆን እፌኑ መልአኪየ ያለ ሚልክያስ ቃለ ዓዋዲ ያለ ኢሳይያስ ነው ። ምነው ነቢይ አለ ቢሉ ያንድ ገንዘብ ሽህ ያላዝብ እንዲሉ ነቢይ የሁሉ ስም ነውና መጽሐፈ ኢሳይያስ ይላል አብነት ኢሳይያስ ነን

ዳባት እንደመምር ሚልክያስ እንደ ልጅ እንደ ደቀ መዝሙር ናቸውና ።

፬ ወሀሎ ዮሐንስ ያጠምቅ በገዳም

፬ ዮሐንስ በምድረ በዳ ያስተምር ነበር ።

ወይሰብክ ጥምቀተ ለንስሐ ወይትኃደግ ሎሙ ኃጢአቶሙ ኃጢአታቸው ሊሠረይላቸው የንስሐ ጥምቀትን ያስተምር ነበር ።

፭ ወየሐውሩ ኀቤሁ ኵሎሙ ሰብአ ይሁዳ ወኢየሩሳሌም ፣ ማቴ ፫ ፣ ፭ ።

፭ የኢየሩሳሌምና የይሁዳ ሰዎች ሁሉ ወደሱ ይሄዱ ነበር ፤ ወያጠምቆሙ ለኵሎሙ በፈለገ ዮርዳኖስ እንዘ ይትአመኑ ኃጢአቶሙ ፤ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ሁሉንም በዮርዳኖስ ወንዝ ያጠምቃቸው ነበር ።

፮ ወልብሱ ለዮሐንስኮ ዘጸጕረ ገመል ማቴ ፫ ፣ ፬ ። ዘሌ ፲፩ ፳፪ ። ሉቃ ፫ ፣ ፲፮ ። ዮሐ ፩ ፣ ፳፯ ። ግብ ፩ ፣ ፭ ።

፮ የዮሐንስ ልብሱ የግመል ጸጕር ነበር ፤ ወቅናቱ ዘአዲም ውስተ ሐቌሁ በወገቡም የሚታጠቀው የኑት መታጠቂያ ነበር ፤ ወሲሳዩ አንበጣ ወመዓረ ጸደና ምግቡም የምድረ በዳ ማርና አንበጣ ነበር ።

፯ ወሰበከ ወይቤ ይመጽእ እምድኅሬየ ዘይጸንዕ እምኔየ ።

፯ ከኔ የበረታ ከኔ በኋላ ይመጣል ፤ ወኢይደልወኒ እድንን ወእፍታሕ ቶታነ እግዕኒሁ እምእገሪሁ ፤ የጫማውን ጠፍር ተጐምብሼ እፈታ ዘንድ የማይገባኝ ፤ ሐተታ እጹር ማቴዎስ እድንን ማርቆስ እፍታሕ ሉቃስ መገናኛው ዮሐንስ ፤ እንዲህ ግን ስለ ሆነ እድንን ይቀድማል እፍታሕ ይከተላል እጹር በመጨረሻ ነው ይህን ተካፍለው ጽፈዋል ።

፰ ወአንሰ አጠምቀክሙ በማይ ፤

፰ እኔ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ፤ ወውእቱሰ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ፤ እሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል ።

በእንተ ጥምቀት ወተመክሮት ዘኢየሱስ ።

፱ ወይእቲ አሚረ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ እምናዝሬት ዘሀገረ ገሊላ ።

፱ በዚያን ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ክፍል ከናዝሬት መጣ ።

ወአጥመቆ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ።

በዮርዳኖስ ወንዝ ዮሐንስ አጠመቀው ።

፲ ወወፂአ እማይ ርእየ ተሰጥቀ ሰማይ ። ሉቃ ፣ ፫ ፣ ፳፪ ። ዮሐ ፣ ፩ ፣ ፴፪ ።

፲ ከወኃውም በወጣ ጊዜ ሰማይ ሲቀደድ አየ ። ሐተታ ። ማቴዎስ ተርኅወ ይላል ከዚህ ማርቆስ ተሰጥቀ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ። ከዚህ ግን ማርቆስ ተሰጥቀ ማለቱ ስለ ክብረ መንፈስ ቅደስ ነው ።

ወወረደ መንፈስ ቅዱስ ከመ ርግብ ወነበረ ዲቤሁ ።

መንፈስ ቅዱስም እንደ ርግብ ወርዶ ተቀመጠበት ።

፲፩ ወመጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል አንተ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወኪያከ ሠመርኩ ።

፲፩ ደስታዬን የማይብህ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ የሚል ድምጽ ከወደ ሰማይ ተሰማ ። ሐተታ ማቴዎስ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ አለው ይላል ፤ ማርቆስ አንተ ውእቱ ወልድየ አለው አለ እንደ ምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎታል ። ማርቆስ ወልድየ አንተ ያለው ትንቢት እንደ ተፈጸመለት ለማጠየቅ አንተ ውእቱ ወልድየ አለው አለ እንጂ ። ፩ም ፣ ነገር እንደ ማርቆስ ከውኃው ሳለ አንተ ውእቱ ወልድየ ብሎታል ። አሁን ወልድ የባሕርይ ልጅነቱን የማያውቅ ሁኖ አይደለም በወልድ ለዮሐንስ ለመናገር ነው እንጂ ። እኮ ዘእስእለክሙ ትንሥኦሙ እምዓለም ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ ትዕቀቦሙ እምእኩይ ባለ ጊዜ አብ የማያውቅ ሁኖ እንዳይደለ በአብ ለሐዋርያት ለመናገር እንደሆነ ። ከውኃው ከወጣ በኋላ እንደ ማቴዎስ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎታል በዮሐንስ ለሕዝቡ ለመናገር ።

፲፪ ወአውፅኦ መንፈስ ሶቤሃ ገዳመ ። ማቴዎስ ፬ ፣ ፩ ፣ ሉቃ ። ፬ ፣ ፩ ።

፲፪ በዚያም ጊዜ መንፈስ ወደምድረ በዳ አወጣው ፤

፲፫ ወነበረ ሐቅለ ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ ፤

፲፫ በምድረ በዳም አርባ ሌሊትና አርባ መዓልት ተቀመጠ ።

ወያሜክሮ ሰይጣን ።

ሰይጣን ይፈታተነው ነበር ።

ወነበረ ምስለ አራዊት ።

ከአራዊት ጋራ ይኖር ነበር ። ርኅቀተ መካኑን ያጠይቃል ።

ወይትለአክዎ መላእክት ።

መላእክትም ያገለግሉት ነበር ።

ዘከመ እኀዘ ኢየሱስ ይስብክ ወይኅረይ ቀደምተ ሐዋርያተ ፤

፲፬ ወእምድኅረ እኀዝዎ ወሞቅሕዎ ለዮሐንስ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ገሊላ ወሰበከ ወንጌለ መንግሥተ እግዚአብሔር ማቴ ፣ ፬ ፣ ፲፪ ፣ ሉቃ ፣ ፬ ፲፬ ዮሐ፣ ፬ ፣ ፵፫ ።

፲፬ ዮሐንስን ይዘው ካሠሩት በኋላ ጌታ ወደ ገሊላ መጥቶ የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌልን አስተማረ ።

፲፭ እንዘ ይብል በጽሐ ጊዜሁ ።
፲፭ ጊዜው ደረሰ ።
ወቀርበት መንግሥተ ሰማያት መንግሥተ ሰማ ያትም ቀረበች ንስሑ ወእመኑ ።
በወንጌል ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ።

፲፮ ወእንዘ የኃልፍ መንገለ ባሕረ ገሊላ ረከቦሙ ለስምዖን ወለእንድርያስ እኁሁ እንዘ ይወድቁ መርበብቶሙ ውስተ ባሕር ፣ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲፰፡ ሉቃ፡፭፡፪ ።

፲፮ በገሊላም ባሕር አጠገብ ሲሄድ ስምዖንን ወንድሙን እንድርያስንም መረባቸውን ከባሕር ሲጥሉ አገኛቸው ።
እስመ መሠግራን እሙንቱ=ዓሣ አጥማጆች ነበሩና ።

፲፯ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ንዑ ትልውኒ ።

፲፯ ጌታም ኑ ተከተሉኝ አላቸው ወእሬስየክሙ መሠግራነ ሰብእ ሰውን እንድታጠምዱ አደርጋችኋለሁ
፲፰ ወኃደጉ መሣግሪሆሙ ወተለውዎ ሶቤሃ
፲፰ ያን ጊዜም መረባቸውን ትተው ተከተሉት
፲፱ ወኃሊፎ ሕቀ እምህየ ረከቦሙ ለያዕቆብ ወለዮሐንስ እኁሁ ደቂቀ ዘብዴዎስ ።

፲፱ ከዚያም ጥቂት እልፍ ብሎ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብን ወንድሙን ዮሐንስንም አገኛቸው ወለሊሁኒ ምስሌሆሙ ።
እሱም ከሳቸው ጋራ ነበር ።
እንዘ ይሠርዑ ወያስተሣንዩ መሣግሪሆሙ ።
መረባቸውን ሲያበጁ ማለት ያደፈውን ሲያጥቡ የተቆረጠውን ሲቀጥሉ ።

፳ ወጸውዖሙ በጊዜሃ ። ወኃደጉ ዘብዴዎስሃ አባሆሙ ምስለ አሳቡ ውስተ ሐመር ወተለውዎ
፳ ጠራቸው።አባታቸውን ዘብዴዎስን ከሚያተኞቹ ጋራ በታንኳ ትተውት ሄደው ተከተሉት ፣ ምስለ አሳቡ ብሎ በማርቆስ ያቀናዋል ያልነው ይህ ነው ።
ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ በቅፍርናሆም ለዘቦቱ ጋኔን ።
፳፩ ወሖሩ ቅፍርናሆም ። ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ፡ ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፴፩ ።
፳፩ ቅፍርናሆም ሄዱ ።
ወቦአ በሰንበት ምኵራበ ወእኀዘ ይምሀሮሙ ፣ ቀዳሚ በምኵራብ ገብቶ ያስተምር ጀመረ ።
፳፪ ወአንከሩ ምሕሮቶ ማቴ ፣ ፯፣ ፳፰ ።
፳፪ ትምህርቱንም አደነቁ ።
እስመ ከመ መኰንን ይሜህሮሙ ወአኮ ከመ ጸሐፍቶሙ እንደ ጸሐፍት ያይደለ ፣ ሥልጣን እንዳለው ያስተምራቸው ነበርና ።
፳፫ ወሀሎ ፩ ብእሲ ዘጋኔን ውስተ ምኵራብ ። ሉቃ፡፬ ፣ ፴፫ ።
፳፫ ከምኵራብ ጋኔን ያደረበት ሰው ነበር ።

፳፬ ወአውየወ ወይቤ ምንት ብየ ምስሌከ ኢየሱስ ናዝራዊ ።

፳፬ የናዝሬቱ ኢየሱስ ካንተ ጋራ ምን ጠብ አለኝ ።
መጻእከኑ ታጥፍአነ ።
ልታጠፋን መጣህን ፣
ነአምረከ ከመ አንተ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ፣ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሆይ ማንም እንደሆንህ እናውቅሃለን ብሎ ጮኸ

፳፭ ወገሠጾ እግዚእ ኢየሱስ ።
፳፭ ጌታም ገሠጸው
ወይቤሎ ተፈጸም አፉከ ዝም በል ።
ወፃእ እምኔሁ
ከሱም ውጣ አለው ።

፳፮ ወአስተራገጾ ውእቱ ጋኔን እኩይ ፣
፳፮ ቢስ ጋኔን አንዘፈዘፈው ሐተታ ይሰማዋልና ጽንዓ ተአምራቱን ለማጠየቅ ፣ አንድም ውደቅ ሌባ ባሉት ጊዜ ከሳንቃው ከመድረኩ እየተማታ እንዲወጣ ፣
ወአውየወ በዓቢይ ቃል ፣
በታላቅ ቃልም ጮኸ ።
ወወፅአ እምኔሁ
ከሱ ወጣ ።

ሐተታ ምኵራቡ ያለ ከተራራ ላይ ነው ያሉ እንደሆነ ሲያስተምር ውሎ ጕባኤ ሲፈታ ከምኵራብ ገብቶ ፈውሶት ሂዷል ምኵራቡ ከተራራው በታች ነው ያሉ እንደሆነ ሲያስተምር ውሎ ከተራራው ወርዶ ከምኵራቡ ገብቶ ፈውሶት ይሄዳል ።

፳፯ ወደንገፁ ኵሎሙ እለ ርእዩ ዘንተ ።
፳፯ ይህን ያዩ ሁሉ አደነቁ ።
ወይቤሉ በበይናቲሆሙ ምንትኑ ዝንቱ ትምህርት ሐዲስ ይህእንግዳ ትምህርት ምድነውእስመ በትእዛዝ ይኤዝዞሙ ለአጋንንት ርኵሳን ከመ ይጻኡ ።
ርኵሳን አጋንንት ይወጡ ዘንድ ያዛቸዋልና ። አንድም ትእምህርት ብለህ ይህ እንግዳ ምልክት ምንድርነው በትእዛዝ ውጡ ብሎ አጋንንትን የሚያዛቸው ወይትኤዘዙ ሎቱ ።
አጋንንትም የሚወጡለት ይህ እንግዳ ምልክት ምንድነው አሉ ።

፳፰ ወተሰምዓ ነገሩ ውስተ ኵሉ በሐውርተ ገሊላ ።
፳፰ ተአምራቱ በገሊላ አውራጃ ሁሉ ተሰማ ።

በእንተ ሐማተ ጴጥሮስ ወካልዓን ሕሙማን እለ ተፈወሱ

፳፱ ወወፂአ እምኵራብ ቦአ ቤተ ስምዖን ።
ማቴ ፡ ፰ ፡ ፲፬ ። ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፴፰ ።

፳፱ ከምኵራብም ወጥቶ ከስምዖን ቤት ገባ ወምስሌሁ እንድርያስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ ።
ያዕቆብና እንድርያስ ዮሐንስም ከሱ ጋራ ነበሩ ።

፴ ወርእያ ሐማቱ ለስምዖን እንዘ ትፈጽን ወትሰክብ ።

፴ የስምዖን አማት ምንሾ ታማ ነበረች ።
ወነገርዎ በእንቲአሃ ።
የሷን ነገር ነገሩት ።

፴፩ ወቀርበ ኀቤሃ ወአኀዘ እዴሃ ወአንሥኣ
፴፩ ቀርቦ እጇዋን ይዞ አሥነሣት ወኃደጋ ፈፀንታ ሶቤሃ ።
ያን ጊዜ ሆድ ዝማዋ ፈጥኖ ተቀት ።
ወተንሥአት ወተልእከቶሙ ። ተነሥታ አገለገለቻቸው ፤ ማቴዎስ ነገርዎ አላለም ከዚህ ማርቆስ ነገርዎ አለ እንደምን ነው ፤ አይጣላም ቢሉ አይጣላም ከመንገድ ሳል ነግረዉታል ከቤት ከገባ በኋላ አልነገሩትም ። ያን ከመንገድ የነገሩትን ይዞ አድኑዋታል ፥ ከቤት ከገባ በኋላ አለመንገራቸውን ሲያይ ማቴዎስ ነገርዎ አላለም ፤ ከመንገድ መንገራቸውን ሲያይ ማርቆስ ነገርዎ አለ ። አንድም ነገር እንደ ማርቆስ ፥ ከመንገድ ባለ ነግረውታል ። ከቤት ገብቶ ነገሩን እሳቸው ያንሱ ብሎ ዝም ብሏል ሁለተኛ ነግረውት ፈዉሷታል ነገሩን ያንሱት ብሎ ዝም ስላለ ማቴዎስ ነገርዎ አላለም ፤ ሁለተኛ መንገራቸውን ሲያይ ማርቆስ ነገርዎ አለ ።

፴፪ ወመስዬ ጊዜ የዓርብ ፀሐይ አምጽኡ ኀቤሁ ኵሎ ድውያነ ወእለሂ እኑዛነ አጋንንት ።
፴፪ ሲመሽ ፀሐይ በሚገባበት ጊዜ ድውያንን ሁሉ ጋኔን ያደረባቸውንም ወደርሱ አመጧቸው ።

፴፫ ወተጋብኡ ኵሎሙ ሰብአ ሀገር ኀበ አንቀጽ
፴፫ ሰዎች ሁሉ ከበር ተሰብስበው
፴፬ ወፈወሶሙ ለብዙኃን ድውያን ወሕሙማን ፡ ሉቃ ፥ ፬ ፡ ፵፩ ።

፴፬ ብዙ ድውያንን አዳናቸው ወአውፅአሙ ለብዙኃን አጋንንት ።
ብዙ አጋንንትንም አወጣቸው ወኢያብሖሙ ይንብቡ ይናገሩ ዘንድ አላሰናበታቸውም ዝም በሉ አላቸው፤
እስመ አእመርዎ ከመ ውእቱ ክርስቶስ ።
ክርስቶስ እንደ ሆነ ስላወቁት ።
፴፭ ወበጽባሕ ተንሥአ ወአሌለየ ጥቀ ወወፂአ ሖረ ሐቅለ ወጸለየ በህየ ።
፴፭ ማለዳ ገሥግሦ ወጥቶ በረሃ ሂዶ በዚያ ጸለየ ።
፴፮ ወዴገንዎ ስምዖን ወእለ ምስሌሁ ፤
፴፮ ስምዖን ከሱም ጋራ የነበሩት ተከተሉት።
፴፯ ወሶበ ረከብዎ ይብልዎ ኵሉ ሕዝብ የኃሥሡከ ።

፴፯ ባገኙት ጊዜ ሁሉ ይሹሃል አሉት ።
፴፰ ወይቤሎሙ መልኡ ንሑር ካልአተኒ አንጉረ
፴፰ ወደሌላውም አገር ተነሥ እንሂድ አላቸው ከመ በህየኒ እሰብክ ።
በዚያም አስተምር ዘንድ ፤
እስመ እንበይነ ዝ ግብር መጻእኩ ።
ስለዚህ ነገር ሰው ሁኛለሁና ።

፴፱ ወሖረ ወሰበከ በምኵራባቲሆሙ ውስተ ኵሉ ገሊላ ።

፴፱ ሂዶ በገሊላ ሁሉ በምኵራብ አስተማረ ።
ወያወፅእ አጋንንተ ።
ጋኔን ያወጣ ነበር ።

፵ ወመጽአ ኀቤሁ ዘለምጽ ማቴ፡ ፰ ፡ ፪ ።
ሉቃ፡ ፭፡፲፪ ።

፵ ለምጽ የያዘው ሰው መጣ ፤
ሰገደ ሎቱ አስተብረከ ወአስተብቍዖ ።
ሰገደ ማለደው ።
ወይቤሎ እግዚኦ እመሰ ፈቀድከ ትክል አንጽሖትየ
አቤቱ ከወደድህስ እኔን ማዳን ይቻልሃል አለው ።

፵፩ ወምህሮ እግዚእ ኢየሱስ ፤
፵፩ ጌታም ራራለት ፤
ወሰፍሐ እዴሁ ወገሠሦ ፤
እጁን ዘርግቶ ዳሰሰው ፤
ወይቤሎ ፈቀድኩ ንጻሕ ፤
እወዳለሁ ዳን አለው ።

፵፪ ወዘንተ ብሂሎ ሐይወ ለምጹ ሶቤሃ ።
፵፪ ይህን በተናገረ ጊዜ ለምጹ ፈጥኖ ዳነ ፤
፵፫ ወገሠጾ ወፈነዎ ወይቤሎ ዑቅ ኢትንግር ወኢለመኑሂ ፤
፵፫ ለማንም ለማን እንዳትነግር አስተውል ብሎ ገሥጾ ሰደደው ።
፵፬ ወሑር ወአፍትን ርእሰከ ለካህን ሌዋ፥፲፬፥፪።
፵፬ ነገር ግን ሂደህ ራስህን ለካህን አስመርምር።
ወአብእ መባዐከ በእንተ ዘነጻሕከ ፤
ስለ ነጻሕም መባሕን ስጥ ።
በከመ አዘዘ ሙሴ ።
ከመ ይኩን ስምዓ ሎሙ ሙሴ እንዳዘዘ መፈራረጃ ይሆንባቸው ዘንድ ፤
ማቴዎስ ዘለምጽን ያስቀድማል ሐማተ ጴጥሮስን ወደኋላ ያደርጋል ማርቆስ ሐማተ ጴጥሮስን አስቀድሞ ዘለምጽን አስከተለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ። ለወንጌልና ለድጓ ተራ የለውም ።
፵፭ ወወፂአ አኀዘ ይሰብክ ወይንግር ብዙኃ እስከ ያነከሩ ኵሉ ሀገር ።
፵፭ ብወጣም ጊዜ ሰው ሁሉ እስኪያደንቅ ብዙ ተናገረ ያወራም ጀመረ ።
ወሰልሶ በዊአ ሀገር ክሡተ ። ተገልጦ ወደ ሀገር መግ

ባቅ ተሣነው ሐቴታኀበሰው ጭቁ ንዌሬ ነበርና እም
ስት ገበያ ሰው ይከተለው ነበርና ።
አላ አፍአ ገዳመ ይነብር ።
ብቻውንስ በገዳም ይገኝ ነበር እንጂ ።
ወይመጽኡ ኀቤሁ ስብእ እምኵሉ ።
ከየቦታውም ሰዎች ሁሉ ወደሱ ይመጡ ነበር ። አንድም ወስዕነ እያልክ መልስ ከሥጋዌ አሰቀድሞ መመስን ተሳነው ከመመሰን በአፍአ ነበር እንጂ አንድም ከሥጋዌ አሰቀድሞ ታይቶ ተአምራት ማድረግ ተሳነው ታይቶ ታአምራት ከማድረግ በአፍአ ነበር እንጂ አንድም ከሥጋዌ አሰቀድሞ በሰው ልቡና ማደር ተሳነው በሰው ልቡና ከማደር በአፍአ ነበር እንጂ ። አንድም በመዓልት በደብረ ዘይት መዋል ተሳነው በመዓልት በምኩራብ ሲያስተምር ይውል ነበር እንጂ አንድም ቤሌሊት በምኩራብ ማደር ተሳነው ሌሊት በደብረ ዘይት ሲጸልይ ያድር ነበር እንጂ ።

በከመ ሐይወ መጻጕዕ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወቦአ ካዕበ ሀገረ ቅፍርናሆም ማቴ፡ ፱፡ ፩ ።

፩ ሁለተኛ ወደቅፍርናሆም ገባ ።
ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል ሶበ ሰምዑ ሰብእ ዜናሁ ከመ ሀሎ ውስተ ቤት ።
ከቤት እንዳለ ከጥቂት ቀን በኋላ ሰዎች ነገሩን በሰሙ ጊዜ ።

፪ ተጋብኡ ኀቤሁ ብዙኃን ሕዝብ እስከ ኢያገምሮሙ መካን ።

፪ ቦታ እስኪጠባቸው ብዙ ሰዎች ወደሱ ተሰበሰቡ ።
ወኢኀበ ኆኅት ።
በደጅም ቢሆን ።
ወኮነ ይነግሮሙ ቃሎ ለእለ መጽኡ ኀቤሁ ።
ወደሱ ለመጡ ነገርን ይነግራቸው ነበር ማለት ወንጌልን ያስተምራቸው ነበር ። አንድም ቃሉ ይላል አካላዊ ቃል ያስተምራቸው ነበር ።

፫ ወአምጽኡ ኀቤሁ ድውየ መጻጕዓ እንዘ ይጸውርዎ በዓራት እርብዕቱ አደው ። ሉቃ፡ ፭፡ ፲፰ ።

፫ አራት ሰዎች ባልጋ ተሸክመው ደዌ የጸናበት ሰው አመጡለት ።

፬ ወሶበ ስዕኑ አብእቶ ኀቤሁ እስመ ጽፉቅ ሰብእ ኀበ ሀሎ እግዚእ ኢየሱስ ።

፬ ጌታ ካለበት ቦታ ብዙ ሰው ነበርና ወደ ጌታ ማቅረብ በተሳናቸው ጊዜ ወጽፉቅ በዋዌ ቤታ እንዲል ።
ዓርጉ ናሀሰ ወነሠቱ ጠፈረ ቤት ወአውረድዎ ምስለ አራቱ ዘዲቤሁ ይሰክብ ውስተ መፃጕዕ ።

ከሰገነቱ ወጥተው ማገሩን አፍርሰው አስፋፍተው ድውዩን ከነአልጋው አገቡት ። አንድም ቤተ ምሕኃይ ቤተ ምክራም አላቸው ። በበጋ የሚያነሡት በክረምት የሚደፉት አለ ያን አንስተው አወረዱት

፭ ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ሃይማኖቶሙ ይቤሎ ለውእቱ መፃጕዕ ወልድየ ተኃድገ ለከ ኃጢአትከ።

፭ ጌታ ሃይማኖታቸውን አይቶ ያን ድውይ ኃጢአትህ ተሰርዮልሐል አለው ።

፮ ወሀለዉ ህየ ጸሐፍት ይነብሩ ኢዮ፡ ፲፬፡ ፫ ኢሳ፡ ፵፫፡ ፳፭ ።

፮ ጸሐፍት ከዚያ ተቀምጠው ነበር ።

፯ ወሀለዩ በልቦሙ ወይቤሉ ምንትኑ ዝ ዘከመዝ ጽርፈተ ይነብብ ።

፯ በልባቸው አሰበው ይህ እንዲህ ያለ ስድብ ለምን ይናገራል ፡ መኑ ይክል ኀዲገ ኃጢአት ዘእንበለ ፩ እግዚአብሔር ።
ያላንድ እግዚአብሔርስ ኃጢአት ማስተስረይ የሚቻለው ማነው አሉ ።

፰ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ በመንፈሱ ከመ ከመዝ ይሔልዩ ወይቤሎሙ ለምንት ከመዝ ትሔልዩ እኩየ በልብክሙ ፡

፰ ጌታም እንዲህ እንዲያስቡ በመንፈሱ ዐውቆ ለምን እንዲህ ክፉን ታስባላችሁ ።

፱ ምንት ይቀልል እምብሂሎቱ ለዝ መፃጕዕ ተኃድገ ለከ ኃጢአትከ ወእምብሂለ ተንሥእ ወንሣእ አራተከ ወሑር በእገሪከ ።

፱ ይህን ድውይ ኃጢአትህ ተሰረየልህ ከማለትና ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል አላቸው ።

፲ ከመ ታእምሩ ከመ ብውህ ሎቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው የኅድግ ኃጢአተ በዲበ ምድር።

፲ በምድር ላይ ኃጢአት ያስተሰርይ ዘንድ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው ልታውቁ ።

፲፩ ወካዕበ ይቤሎ ለውእቱ ድውይ ለከ፤እብለከ ተንሥእ ወንሣእ አራተከ ውእቱ ቤተከ ።

፲፩ ዳግመኛ ያን ድውይ ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ወደቤትህ ሂድ እልሃለሁ አለው ።

፲፪ ወተንሥአ ሶቤሃ ወነሥአ አራቶ ወወፅአ በቅድመ ኵሎሙ ሰብእ ።

፲፪ ያን ጊዜውንም ተነሥቶ አልጋውን ተሸክሞ በሰው ሁሉ ፊት ወጣ ።
ወአንከሩ ኵሎሙ ሕዝብ ወአእኰትዎ ለእግዚአብሔር ፤ ሰዎች ሁሉ አድንቀው እግዚአብሔርን አመሰገኑት ።
ወይቤሉ ኢርኢነ ግሙራ ዘከመዝ ።
ከቶ እንዲህ ያለ አላየንም አሉ ።

ዘከመ ተጸውዖ ሌዊ ።

፲፫ ወአምዝ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ ካዕበ መንገለ ጽንፈ ባሕር ።

፲፫ ከዚህ በኋላ ጌታ ወደ ባሕር ዳር ወጣ ።
ወሖሩ ኀቤሁ ኵሉ ሕዝብ ።
ሕዝቡ ሁሉ ወደሱ ሄዱ ።
ወመሀሮሙ ።
አስተማራቸው ።

፲፬ ወኃሊፎ እምህየ ርእዮ ለሌዊ መጸብሐዊ ወልደ እልፍዮስ እንዘ ይነብር ኀበ ምጽባሕ ። ማቴ፡፱ ፡ ፱ ፡ ሉቃ ፡ ፭ ፡ ፳፯ ።

፲፬ ከዚያም አልፎ ሲሄድ የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን ከሚያስገብርበት ቦታ ተቀምጦ አየው ። ሐተታ፥ ማቴዎስን ወልደ ዲቍ ይለዋል ከዚህ ወልደ እልፍዮስ አለው እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ። ላንድ ሰው ሁለት ስም አለውና ። አንድም አንዱ ያባቱ አንዱ የእያቱ ።
ወይቤሎ ንዓ ትልወኒ ።
ተከተለኝ አለው ፤ ወተንሢኦ ተለዎ ተነሥቶ ተከተለው ።

፲፭ ወእንዘ ይመስሕ ውስተ ቤቱ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፭ ከዚህ በኋላ ጌታ በቤቱ ተቀምጦ ሲበላ ፤
ሀለው ምስሌሁ ብዙኃን ኃጥአን ወመጸብሐን ዘረፈቁ ምስለ እግዚእ ወአርዳኢሁኒ ።
ብዙ ቀራጮችና ኃጥአን ከጌታና ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ተቀምጠው የበሉ ነበሩ ።
ወብዙኃን እሙንቱ እለ ይተልውዎ ፤
የተከተሉትም ብዙ ነበሩ ።
ወኮኑ ይተልውዎ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ።
ጸሐፍት ፈሪሳውያንም ተከትለውት ነበር ፤

፲፮ ወርእዮሙ ከመ ይበልዕ ምስለ ኃጥአን ወመጸብሐን ።

፲፮ ከኃጥአንና ከመጸብሐን ጋራ ሲበላ ባዩት ጊዜ ፤ ይቤልዎሙ ለአርዳኢሁ ለምንት ይበልዕ ወይሰቲ ሊቅክሙ ምስለ ኃጥአን ወመጸብሐን ፤ ደቀ መዛሙርቱን መምህራችሁ ከመጸብሐን ጋራ ለምን ይበላል አሏቸው ፤ ማቴዎስ አርድእተ ዮሐንስ ጠየቁት ይላል ፤ ከዚህ ማርቆስ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ጠየቁት አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ፤ ፈሪሳውያን አርድእተ ዮሐንስን ጠይቁልን ብለዋቸው ጠይቀውታል ፤ ማርቆስ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ጠየቁት ማለቱ ኋላ ተከትረው ሂያው ጠይቀውታል እማላጅ የሰደደ ሰው አብሮ ተከትሎ ሂዶ እንዲናገር አንድም ነገር እንደ ማርቆስ ነው ፈሪሳውያን ሂደው ጠይቀውታል ባይመልስላቸው ለኛስ አልመለሰልንም እናንተ ሂዳችሁ ጠይቁት ብለዋቸው አርድእተ ዮሐንስ ሂደው ጠይቀውታል እንጂ ማቴዎስ ይህን ተካፍለው ጽፈዋል ።

፲፯ ወሰሚዖ እግዚእ ኢየሱስ ይቤሎሙ ሕሙማን ይፈቅድዎ ለዓቃቤ ሥራይ ወአኮ ጥዑያን ፩፥ጢሞ፥ ፩፥፲፭ ።

፲፯ ጌታም ይህን ሰምቶ ባለመድኃኒትን ድውያን ይሹታል እንጂ ጤነኞች አይሹትም ። ወኃጥአን አጸውዕ መጻእኩ ወአኮ ጸድቃነ ።
ጻድቃንን ያይደለ ኃጥአንን ልጠራ መጥቻለሁ አላቸው ።

በእንተ ጾም ዘክርስቲያን ።

፲፰ አርዳኢሁስ ለዮሐንስ ወእለሂ ፈሪሳውያን ኮኑ ይጸውሙ ።

፲፰ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና የፈሪሳውያን ወገኖች ይጦሙ ነበርና ።
ወመጽኡ ወይቤልዎ በእፎ አርዳኢሁ ለዮሐንስ ወአርዳኢሆሙ ለፈሪሳውያን ይጸውሙ ።
የፈሪሳውያንና የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለምን ይጦማሉ ።
ወአርዳኢከ ኢይጸውሙ ።
ደቀ መዛሙርትህ ግን አይጦሙም አሉት ።

፲፱ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ
ይክሉኑ ደቂቀ ለመርዓዊ ጾዊመ እምጣነ ሀሎ መርዓዊ ምስሌሆሙ ።

፲፱ ጌታም የሰርግ ልጆች ከሙሽራ ጋራ ሳሉ መጾም ይቻላቸዋልን አላቸው ።

፳ ወባሕቱ ይመጽእ መዋዕል አመ ይነሥእዎ ለመርዓዊ እምኔሆሙ ። ማቴ፥፱፥፲፭ ። ሉቃ ፭፥ ፴፭።

፳ ነገር ግን ሙሽራው ከሳቸው የሚለይበት ዘመን ይመጣል ።
ወአሜሃ ይጸውሙ ፤
ያን ጊዜ ይጦማሉ ።

፳፩ ወአልቦ ዘይጠቅብ ግምደ ድርጓሃ ውስተ ስጠተ ልብስ ብሉይ ።

፳፩ ባረጀ ልብስ ቀዳዳ አዲስ እራፊ የሚሰፋ የለም ።
ወእመ አኮ ያነቅዖ ጥቅቡ ሐዲስ ለብሉይ ።
ያለዚያ ግን ማለት ቢሰፋት ግን አዲሱ እራፊ አሮጌውን ይቀደዋል ።
ወየዓብዮ ለስጠቱ ።
ቀዳዳውን ያሰፋዋል ።

፳፪ ወአልቦ ዘይወዲ ወይነ ሐዲሰ ውስተ ዝቅ ብሉይ ።

፳፪ ጉሽ ጠጅ ባረጀ ረዋት የሚያኖር የለም።
እስመ ያነቅዖ ወይን ሐዲስ ለዝቅ ብሉይ ።
ጉሽ ጠጅ ያረጀውን ረዋት ይቀደዋልና ።
ወወይንሂ ይትከዓው ። ጠጁም ይፈሳልና ።

ወዝቁኒ ይትኃጐል ።
ረዋቱም ይጠፋልና ።
ወባሕቱ ሰወይንሰ ሐዲስ ውስተ ዝቅ ሐዲስ ይወድይዎ ፤ አዲሱን ጠጅ ግን ባዲስ ረዋት ይኾሙታል ፡ ማቴ ፥ ፲፯ ፥ ፱ ፥ ወይትዓቀቡ በበ ይናቲሆሙ ። እሉ በሳቸው ይጠባበቃሉ ።

በእንተ ሰዊተ ሥርናይ ወሰንበት ።

፳፫ ወእምዝ ወፈረ እግዚእ ኢየሱስ በሰንበት ማእከለ ገራውሀ ፤

፳፫ ከዚህ በኋላ ጌታ ቅዳሜ በርሻ መካከል ሄደ።
ወአርዳኢሁኒ ምስሌሁ ።
ደቀ መዛሙርቱም ከሱ ጋራ ነበሩ ፤
ወእንዘ ይምሐው ሰዊተ ወይበልዑ ፤
እሸት እያሹ ይበሉ ጀመር ፤
ወይጼሐሉ ሎቱ ፍኖተ ፤
የተቃወሰውንም ያቃኑለት ጀመረ ፤

፳፬ ወይቤልዎ ፈሪሳውያን ርኢ ዘይገብሩ አርዳኢከ ዘኢይከውን ገቢረ በሰንበት ።
፳፬ ፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርትህ ቅዳሜ ሊሠሩት የማይገባ ሥራ ሲሠሩ አስተውል አሉት ።

፳፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ግሙራ ኢያንበብክሙኑ ዘገብረ ዳዊት አመ ርኀበ፡፩ነገ ፳፩።
፳፭ ዳዊት በተራበ ጊዜ ያደረገውን ከቶ አል ተመለከታችሁም ።
ወውእቱኒ ።
እሱም ።
ወእለ ምስሌሁ ፤
ከሱም ጋራ ያሉ ፤
፳፮ ዘከመ ቦአ ቤተ እግዚአብሔር እንዘ አብያታር ሊቀ ካህናት ወበልዐ ኅብስተ መሥዋዕት ዘኢይደልዎ ሰበሊዕ ዘእንበለ ለካህናት ለባሕቲቶሙ ወወሀቦሙ ለእለ ምስሌሁ ወበልዑ ፡ ዘሌ፥፳፬፡፲።
፳፮ አብያታር ሊቀ ካህናት ሁኖ ሳለ ከቤተ እግዚአብሔር ገብቶ ለካህናት ብቻ ይገባቸዋል እንጂ ሊበላው የማይገባውን መሥዋዕቱን በልቶ ከሱም ጋራ ላሉ ሰጥቷቸው እንደበሉ ዳዊት ያደረገውን ከቶ አልተመለከታችሁምን ፤ ሐተታ ሊቀ ካህናቱ አቤሜሌክ አይደለም ቢሉ ምሉና ዱግ ሁነው ተሹመው ነበር ።
፳፯ ወይቤሎሙ ሰንበትሰ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት ወአኮ ሰብእ በእንተ ሰንበት ።
፳፯ ሰንበት ለሰው ተፈጥራለች እንጂ ሰው ስለሰንበት አልተፈጠረም አላቸው ።
፳፰ ወወልደ ዕጓለ እመሕያው ውእቱ እግዚእ ለሰንበት ፤
፳፰የሰንበት ጌታዋ የሰው ልጅ ነው ።

ምዕራፍ ፫ ።

በእንተ ዘየብሰት እዴሁ ፡

፩ ወቦአ ካዕበ ምኵራበ በሰንበት ማቴ፥፲፪፥፱ ። ሉቃ ፮ ፥ ፯ ።
፩ ሁለተኛ ወደ ምኵራብ ቅዳሜ ገባ ።
ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ ዘየብሰት እዴሁ ።
ከዚያም እጁ የሰለለ ሰው ነበር ፡
፪ ወይትዓቀብዎ ለእመ ይፌውሶ በሰንበት ከመ ያስተዋድይዎ ።
፪ ሊያሳጡት ቅዳሜ ይፈውሰው እንደሆነ ብለው ይጠብቁት ነበር ።

፫ ወይቤሎ ለውእቱ ብእሲ ዘጽውስት እዴሁ ተንሥእ ወቁም ማእከለ ።
፫ ያን እጁ የሰለለች ሰው ተነሥተህ ከመካከል ቁም አለው ፤
፬ ወይቤሎሙ ይከውንኑ በሰንበት ገቢረ ሠናይ አው ገቢረ እኩይ ።
፬ ቅዳሜ በጐ ሥራ መሥራት ይሻላልን ወይም ክፉ ሥራ መሥራት ፤
አሕይዎ ነፍስኑ ወሚመ ቀቲል የሚገባ ነፍስ መግደል ነውን ወይስ ማዳን አላቸው ።
ወአርመሙ ።
ዝም አሉ ፡ ማቴዎስ ይከውንሁ ብለው አሳቸው ጠየቁት ይላል ማርቆስ እሱ ጠየቃቸው አለ እንዴ ምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ይከውንሁ ብለው ቢጠይቁት ምሳሌ በግዕን ነግሮ ተንሥእ ወቁም ማእከለ ብሎ ይከውንሁ አላቸው አርመሙ ዝም አሉ ስፋሕ እዴከ ይለዋል አንድም እንደ ማቴዎስ ይከውንሁ ቢሉት ተንሥእ ወቁም ማእከለ ብሎ ምሳሌ በግዕን ነገራቸው ዝም አሉ ስፋሕ እዴከ ይለዋል ፡ አንድም እንደ ማቴዎስ ይከውንሁ ቢሉት መልሶ ይከውንሁ ገቢረ ሠናይ በሰንበት አሕይዎ ነፍስኑ ወሚመ ቀቲል አላቸው ። ወአርመሙ ዝም አሉ ምሳሌ በግዕን ነግሮ ተንሥእወቁም ማእከለ ብሎ ስፋሕ እዴከ ይለዋል ።

፭ ወነጸሮሙ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይትመዓዕ ወይቴክዝ በእንተ ዑረተ ልቦሙ ።
፭ ስለ ልቡናቸው ድንቁርና እያዘነ ጌታ በቁጣ አያቸው ።

ወእምዝ ይቤሎ ለውእቱ ብእሲ ስፋሕ እዴከ ወሰፍሐ እዴሁ ። ያን ሰው እጅህን ዘርጋ አለው እጁን ዘረጋ ።
ወሐይወት ወኮነት ከመ ካልዕታ ድና እንደ ሁለተኛይቱ ሆነች ፤
፮ ወወፂኦሙ ፈሪሳውያን ሶቤሃ ተማከሩ ምስለ ሰብአ ሄሮድስ ከመ ይቅትልዎ ።

፮ ፈሪሳውያን ወጥተው ከሄሮድስ ሰዎች ጋራ ሊገሉት ተማከሩ ።

በእንተ ካልዓን ተአምራት ዘኢየሱስ ፤

፯ ወተግኅሠ እግዚእ ኢየሱስ ምስለ አርዳኢሁ መንገለ ባሕር ።

፯ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ወደ ባሕር ሄደ

፰ ወተለውዎ ብዙኃን ጥቀ እምገሊላ ወእምይሁዳ ወእምኢየሩሳሌም ።

፰ ከይሁዳና ከገሊላ ከኢየሩሳሌም እጅግ ብዙ ሰዎች ተከተሉት ። ወእምኤዶምያስ ወእማዕዶተ ዮርዳኖስ ።

ከዮርዳኖስ ማዶና ከኤዶምያስም ።

ወእምጢሮስ ወእምሲዶና ።

ከሲዶናና ከጢሮስም ።

ወብዙኃን ጥቀ መጽኡ ኀቤሁ ሰሚዖሙ ኵሎ ዘገብረ ያደረገውን ሁሉ የሰሙ እጅግ ብዙ ሰዎች ናቸው ።

፱ ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ያጽንሑ ሎቱ ሐመረ ከመ ኢይትጋፍዕዎ ሰብእ ።

፱ ሰዎች እንዳይገፉት ደቀ መዛሙርቱን መርከብ አቆዩኝ አላቸው ።

፲ እስመ ለብዙኃን አሕየዎሙ

፲ ብዙ ሰዎችን አድኖዋቸዋልና ።

ወኮኑ ይትጋፍዕዎ እስከ ይወድቁ ዲቤሁ ።

ከላዩ ላይ እስቲወድቁ ድረስ ይጋፉት ነበር ።

ወአስተብቍዕዎ ከመ ይግሥሥዎ ኵሎሙ ሕሙማን

ሕሙማን ሁሉ ሊዳስሱት ይማልዱ ነበር ።

፲፩ ወእለሂ እኩያን አጋንንት ርኩሳን እምከመ ርእይዎ ይሰግዱ ሎቱ ።

፲፩ ርኩሳን አጋንንት ያደሩባቸው ሁሉ ያዩት እንደሆነ ይሰግዱለት ነበር ።

ወእንዘ ይጸርሑ ወይብሉ አማን አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ።

ጮኸው የእግዚአብሔር ልጅ በውነት አንተ ነህ አሉ ፤

፲፪ ወኮነ ብዙኃ ይጌሥጾሙ ከመ ኢያግህድዎ

፲፪ እንዳይገልጡት ፤

ወከመ ኢይከሥቱ ግብሮ ፤

ሥራውንም እንዳይገልጡ ብዙ ገሠጻቸው ።

በእንተ ዘከመ ኀረዮሙ ለሐዋርያት ።

፲፫ ወዓርገ ደብረ ወጸውዓ እለ ፈቀደ ። ማቴ ፲ ፡ ፩ ፤ ሉቃ ፮ ፡ ፲፫ ፡ ፱ ፡ ፩ ።

፲፫ ከተራራ ወጥቶ የወደዳቸውን ጠራ ማለት ሹመት ሽረት አደረገ ወመጽኡ ኀቤሁ ።

ወደሱ ሄዱ ።

ወኀረየ ፲ተ ወ፪ተ ወሰመዮሙ ሐዋርያተ ፤

ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጠ ።

ወረሰዮሙ ከመ የሀልዉ ምስሌሁ ።

ከሱም ጋራ እንዲኖሩ አደረጋቸው ። ሐተታ ደጃዝማች በተሾመ ጊዜ ፈጥኖ እንዲይሄድ ወግ ታሪክ ሲያጠና እንዲሰነብት ።

፲፬ ወፈነዎሙ ይስብኩ ።

፲፬ ያስተምሩ ዘንድ ላካቸው ።

፲፭ ወአብሐሙ ያውፅኡ አጋንንተ ወይፈውሱ ዱያነ ።

፲፭ አጋንንትን ያወጡ ዘንድ ድውያንንም ይፈውሱ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው ።

፲፮ ወሰመዮሙ በበአስማቲሆሙ ፤

፲፮ በየስማቸው ጠራቸው ።

ወሰመዮ ለስምዖን ጴጥሮስ

ስምዖንን ጴጥሮስ አለው

፲፯ ወለያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ወለዮሐንስ እኁኁ ሰመዮሙ በአኔርጌስ ።

፲፯ ያዕቆብንም የዘብዴዎስን ልጅ ዮሐንስንም የያዕቆብን ወንድም በአኔርጌስ አላቸው ደቂቀ ነጐድጓድ ብሂል የነጐድጓድ ልጆች ማለት ነው ፤ ሐተታ ፡ በርጌስ ማለት በዕብራይስጥ ልሳን ልጅ ማለት ነው ። ጌስ ደቂቀ ነጐድጓድ ማለት ነው አኔ ትርፍ ቀለም ነው ። እልመስጠአግያ እንደማለት አልም ትምህርት ስጠ ትርፍ እግያ ኅቡእት እንደሆነ ደቂቀ ነጐድጓድ አለ ፤ ደቂቀ ምሥጢር ደቂቀ መለኮት ሲል ነው ። ደቂቀ ነጐድጓድ ማለቱ በምሳሌ ነው ርጡብ ጢስ ከርጡብ ምድር ይቡስ ጢስ ከይቡስ ምድር ወጥቶ አንድ ደመና ይሆናል ከውቅያኖስ ውኃ ጠልፎ ሲወጣ ነጐድጓድ ያሰማል ፤ እኒህም ከቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥት ተወልደው ቢያስተምሩ ተሰምተዋልና ደቂቀ ነጐድጓድ አላቸው ።

፲፰ ወእንድርያስ ፡

፲፰ እንድርያስ

ወፊልጶስ ።

ፊልጶስ ፡

ወበርተሎሜዎስ ፡

በርተሎሜዎስ ፤

ወማቴዎስ

ማቴዎስ ፤

ወቶማስ

ቶማስም

ወያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ

የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ

ወታዴዎስ

ታዴዎስ

ወስምዖን ቀነናዊ

ቀነናዊ ስምዖን ።

፲፱ ወይሁዳ አስቆሮታዊ ዘውእቱ ዘአግብኦ

፲፱ የአስቆሮት ሰው የሚሆን ያሲያዘው ይሁዳ

፳ ወበዊአ ቤተ መጽኡ ካዕበ ብዙኃን እሕዛብ እስከ ኢያበውህዎ ይብልዑ እክለ ።

፳ ክቤት በገባ ጊዜ እንጀራ ይበላ ዘንድ እስኪሳነው ድረስ ብዙ አሕዛብ ሁለተኛ መጡ ። ዘከመ አስተዋደይዎ ለኢየሱስ ከመ ያወፅኦ አጋንንተ በብዔል ዜቡል ።

፳፩ ወሰሚዖሙ አዝማዲሁ መጽኡ የአኃዝዎ
፳፩ ዘመዶቹም ሰምተው ሊይዙት መጡ ።
እስመ ስሕወ ልቡ ይቤልዎ ።
ልቡሻ እለው ብለዋልና ፣

፳፪ ወጸሐፍትኒ እለ ወረዱ እምኢየሩሳሌም ይቤሉ ብዔል ዜቡል አኀዞ ። ማቴ ፣ ፱፣ ፴፬ ።

፳፪ ከኢየሩሳሌም የወረዱ ጸሐፍት ብዔል ዜቡል አድሮበታል ።

ወበመልአኮሙ ለአጋንንት ያወፅአሙ ለአጋንንት ። በሰይጣን አለቃ ሰይጣናትን ያወጣል አሉ ።

፳፫ ወጸውዖሙ እግዚእ ኢየሱስ ወመሰለ ሎሙ ወይቤሎሙ እፎ ይክል ሰይጣን ለሰይጣን አውፅኦቶ ፤

፳፫ ጌታ ጠርቶ ሰይጣን ሰይጣንን ማውጣት እንደምን ይቻለዋል ብሎ ምሳሌ መስሎ ነገራቸው ።

፳፬ ወመንግሥትኒ ዘበበይናቲሃ ትትናፈቅ ኢትቀውም ይእቲ መንግሥት ።

፳፬ እርስ በርሱዋ የምትከፋፈል መንግሥት አትጸናም ።

፳፭ ወእመኒ ቤት ተናፈቀት በበይናቲሃ ኢትቀውም ይእቲ ቤት ፤

፳፭ ቤትም እርስ በርሷ ብትከፋፈል ያች ቤት አትጸናም ።

፳፮ ወሰይጣንሂ ለእመ ተንሥአ በበይናቲሁ ወተናፈቀ ኢይቀውም ።

፳፮ ሰይጣንም እርስ በርሱ ቢጣላ ቢለያይም አይጠናም ።
አላ ማኅለቅተ ይረክብ ።
ተፍጻሜተ ሲል ነው ። ፍጻሜ አለበት እንጅ ።

፳፯ ወአልቦ ዘይክል በዊአ ቤተ ኃያል ወበርብሮተ ንዋዩ ለእመ ኢቀደመ አሲሮቶ ለኃያል ።

፳፯ ብርቱውን አስቀድሞ ካላሰረ ወደብርቱ ቤት መግባት ገንዘቡንም መዝረፍ የሚቻለው የለም ወትምግዝ ይበረብር ቤቶ ።
ከያዘው በኋላ ግን ቤቱን ይብዘብዛል ፣

፳፰ አማን እብለከሙ ኵሉ ኃጢአት ወፅርፈት ይትኃደግ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ፣ ማቴ ፲፪ ፣ ፴፩ ። ሉቃ. ፲፪ ፣ ፲ ። ዮሐ. ፫፣፲፯ ።

፳፰ ኃጢአት ሁሉ ለሰው ልጅ እንዲሰረይ እውነት እነግራችኋለሁ ።

፳፱ ወዘሰ ጸረፈ ዲበ መንፈስ ቅዱስ ኢይትኃደግ ሎቱ ለዓለም ፤

፳፱ መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ግን ለዘለዓለም ስርየት የለውም ወይትኴነን በደይን ለዝልፉ ። በገሃነም የዘወትር ፍርድ ይፈረድበታል እንጂ ።

፴ እስመ ይቤልዎ ጋኔን ርኩስ አኃዞ ።
፴ ርኩስ ጋኔን አድሮበታል ብለውታልና ።

በእንተ አዝማዲሁ ለኢየሱስ

፴፩ ወመጽኡ እሙ ወአኃዊሁ ወቆሙ አፍአ።
፴፩ ወንድሞቹና እናቱ መጥተው በውጭ ቆሙ እስመ ስህወ ልቡ ይቤሉ ይቤልዎሙ መጽኡእሙ ወአኃዊሁ ብለህ ግጠም ወለአኩ ኀቤሁ ይጸውዕዎ ሊጠሩት ማለት ጥሩልን ብለው ላኩ ፣
ወይነብሩ ብዙኃን ሰብእ ምስሌሁ ።
ብዙ ሰዎች ከሱ ጋራ ተቀምጠው ነበር ።

፴፪ ወይቤልዎ ናሁ እምከኒ ወአኃዊከኒ አፍአ ይቀውሙ ወየኃሥሡከ

፴፪ እነሆ እናትህና ወንድሞችህ በውጭ ቆመው ይሹሀል አሉት ።

፴፫ ወአውሥአ ወይቤሎሙ መኑ ይእቲ እምየ
፴፫ እናቴ ማናት ፤
ወእለ መኑ እሙንቱ አኃውየ ፤
ወንድሞቼስ እነማናቸው ብሎ መለሰላቸው ሐተታ፣ ማቴዎስ የነገረው አንድ ነው ይላል ማርቆስ ብዙ አለ እንደምነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ የነገረው አንድ ይሁዳ ነው ፣ ማርቆስ ብዙ ማለቱ መናገር የሁሉ ፈቃድ ከሆነ ብሎ ነው ።

፴፬ ወነጸሮሙ ለእለ ይነብሩ ዓውደ ወይቤሎሙ ነዮሙ እምየኒ ወአኃውየኒ ።

፴፬ በዙሪያው ተቀምጠው ወደነበሩት አይቶ እነሆ እናቴም ወንድሞቼም እላቸው ።

፴፭ እስመ ኵሉ ዘይገብር ፈቃዶ ለእግዚአብሔር ውእቱ እኁየኒ ወእኅትየኒ ወእምየኒ ፣
፴፭ ወንድሜም እኅቴም እናቴም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ ነው ።

በእንተ ምሳሌ ዘራዒ

ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወአኀዘ ካዕበ ይምሐሮሙ ለአሕዛብ እንተ መንገለ ባሕር ። ማቴ ፲፫ ፣ ፩ ሉቃ ፰ ፣ ፬ ።

፩ ዳግመኛ በባሕር አጠገብ ያስተምራቸው ጀመር ።
ወተጋብኡ ኀቤሁ ብዙኃን ሰብእ እስከ ሶበ የዓርግ ውስተ ሐመር ወይነብር ።
ከመርከብ ወጥቶ እስኪቀመጥ ብዙ ሰዎች ወደሱ ተሰበሰቡ ። ወኵሉ ሰብእ ውስተ ሐይቅ ይቀውሙ ሕዝቡ ሁሉ ከወደቡ ተቀምጠው ነበር ።
፪ ወመሐሮሙ ወመሰለ ሎሙ ብዙኃ ፣
፪ ብዙ መስሎ አስተማራቸው ።

፫ ወይቤሎሙ እንዘ ይሜሕሮሙ ስምዑ ፤
፫ ሲያስተምራቸውም ስሙ አላቸው ።
ወፈረ ይዝራእ ዘይዘርእ ፣
የሚዘራ ሊዘራ ወጣ ።

፬ ወእንዘ ይዘርዕ ቦ ዘወድቀ ውስተ ፍኖት ።
፬ ሲዘራ ከመንገድ የወደቀ ዘር አለ ፣
ወመጽኡ አዕዋፍ ወበልዕዎ ፣
አዕዋፍም መጥተው የበሉት ፤

፭ ወቦ ዘወድቀ ዲበ ኰኵሕ ኀበ አልቦ መሬት ብዙኀ ።
፭ ብዙ መሬት ከሌለበት ጭንጫ የወደቀ ።
ወፍጡነ በቈለ ፣
ፈጥኖም የበቀለ ዘር አለ ፣
እስመ አልቦ ዕመቅ ለመሬቱ
ለመሬቱ ጥልቅነት የለውምና ፣
፮ ወሠረቀ ፀሐይ አውዓዮ ፣
፮ ፀሐይ በወጣም ጊዜ ደረቀ ።
እስመ ኢኮነ ዕሙቀ መሬቱ መሬቱ ጥልቅ አይደለምና
ወአልቦ ሥርው ፤
ሥር የለውምና ።
የብሰ ፤ ደረቀ
፯ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ሦክ ወሐነቆ ሦክ ኢፈረየ
፯ ከሾህ ውስጥ ወድቆ እሾህ አንቆት ያላፈራም ዘር አለ ።
፰ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ሠናይት
፰ ከመልካም ምድር የወደቀ፤
ወበቈለ ። የበቀለ
ሠልሕቀ ። ያደገ
ወፈረየ ። ያፈራ
ወወሀበ ፍሬ ።
ፍሬውን ያቋረጠ ዘር አለ ።
በ ዘ፴ ። ሠላሳ ያፈራ አለ ፣
ወበ ዘ፷ ። ስሳም ያፈራ አለ ።
ወበ ዘ፻ ።
መቶም ያፈራ አለ ።

፱ ወይቤሎሙ ዘቦ እዝን ሰሚዓ ለይስማዕ።
፱ ጆሮ ያለው ይስማ አላቸው ።
፲ ወሶበ ተባሕተወ ተስእልዎ እለ ኮኑ ምስሌሁ ምስለ ፲ቱ ወ ፪ቱ እርዳኢሁ ምሳሌሁ ለዝንቱ ነገር ፤
፲ ብቻውንም በሆነ ጊዜ ከሱም ጋራ የነበሩት ካሥራሁለቱ ጋራ ምሳሌውን ጠየቁት ።
፲፩ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለክሙ ተውህበ ታእምሩ ምሥጢራ ። ለመንግሥተ እግዚአብሔር ።

፲፩ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ለናንተ ተሰጥቷችኋልና ።
ወለእለ እፍእቱ በምሳሌ ይከውኖሙ ኵሉ ።
በውጭ ላሉ ግን ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል ።

፲፪ ወርእየ ይርአዩ ወኢይርእዩ ። ኢሳ ፮፥፱ ማቴ ፲፫፥፲፬ ዮሐ ፲፪፥፵ ግብ ፳፰፥፳፮ ሮሜ ፲፩፥፰።

፲፪ ማየትን አይተው እንዳይመለከቱ ።
ወሰሚዓ ይሰምዑ ወኢይሌብው ።
መስማትም ሰምተው እንዳያስተውሉ ።
ከመ ኢይነስሑ ።
እንዳይመለሱ ።
ወኢይሣሃሎሙ ይቅር እንዳይላቸው ። ወኢይትኃደግ ሎሙ ኃጢአቶሙ ።
ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ።

፲፫ ወይቤሎሙ ኢተአምሩኑ ዛተ ምሳሌ ።
፲፫ ይህን ምሳሌ ዐታውቁምን ።
እፎ እንከ ተአምሩ ኵሎ አምሳለ ።
ምሳሌውን ሁሉ እንደምን ታውቃላችሁ ማለት ይህን ሳታውቁ ሌላውን እንደምን ታውቃላችሁ ይህን ሳታውቁ ሌላውን ታውቁን አላቸው ።

፲፬ ዘይዘርዕሰ ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ ፣
፲፬ ዘሪው ቃለ እግዚአብሔር ነው ።

፲፭ ወእሉ እሙንቱ እለ ውስተ ፍኖት ኀበ ተዘርዐ ቃል እምከመ ሰምዑ ቃለ ይመጽእ ሰይጣን ሶቤሃ ወይነሥእ እምልቦሙ ቃለ ተዘርዓ ።

፲፭ በመንገድም የተመሰሉ ቃል የሚዘራበት የተባሉ ከሰሙ በኋላ ሰይጣን ፈጥኖ መጥቶ የተዘራውን ቃል ከልባቸው የሚወስድባቸው ናቸው ።

፲፮ ወእሉ ካዕበ እሙንቱ ዘውስተ ኰኵሕ ተዘርዑ እለ ይሰምዑ ቃለ ወይትዌከፍዎ ሶቤሃ በፍሥሐ ።

፲፮ ዳግመኛም በጭንጫ የተዘሩትን ቃል ሰምተው ለጊዜው ደስ ብሏቸው የሚቀበሉት ናቸው ።
፲፯ ወአልቦ ሥርው ።
፲፯ ሥር ግን የላቸውም ።
ወጊዜሃ ዳዕሙ እሙንቱ
ለጊዜው ናቸው እንጂ ፤
ወእምከመሰ ኮነ ምንዳቤ ወስደት በእንተዝ ቃል የዓልው ሶቤሃ ።
ስለዚህ ነገር ስደትና መከራ የሆነ እንደሆነ ግን ፈጥነው ይክዳሉ ።

፲፰ ወእሉ እሙንቱ እለ ውስተ ሦክ ተዘርዑ እለ ይሰምዕዎ ለቃል ።

፲፱ ወሕሊና ዝንቱ ዓለም ወፍትወተ ብዕል ወባዕዳንኒ ኵሉ ፍትወት ይበውእዎ ወየሐንቅዎ ለቃል ። ፩ ፡ ጢሞ ፮፥፲፯ ።

፲፱ በሾህ የተዘሩ ቃልን ሰምተው ብልጽግና መውደድና ።

፲፱ የዚህ ዓለም አሳብ ሌላውም መመኘት ሁሉ መጥቶ ነገሩን የሚያንቀው ነው ።
ወኢይፈሪ ።
አያፈራም ።

፳ ወእሉ እሙንቱ እለ ውስተ ምድር ሠናይት ተዘርዑ እለ ይሰምዑ ቃለ ወይትዌከፍዎ፥

፳ በመልካም ምድር የዘሩት ግን ቃልን ሰምተው የሚቀበሉት ወይፈርዩ ። የሚያፈሩ

፩ዱ ፴ ።	አንዱ ሠላሳ ፥
ወ፩ዱ ፷ ፥	አንዱ ስሳ ።
ወ፩ዱ ፻ ፥	አንዱ መቶ ፥

፳፩ ወይቤሎሙ ቦኑ ዘየሐቱ ማኅቶተ ወያነብራ ታሕተ ከፈር ። ማቴ ፭፥፲፭፥ ሉቃ ፰፥፲፮ ፥

፳፩ እንቅብ ቅርጫት ሊደፋባት ፋና የሚያበራ የለም ። እንደዚህም ሁሉ ላይተረጐም የሚመስል የለም ፥
አላ ያነብርዋ ዲበ ተቅዋማ ፥
ከመቅረዝ ላይ ሊያኖሩት ነው እንጂ ሊተረጐም ነው እንጂ ፥

፳፪ ወአልቦ ኅቡእ ዘኢይትከበት ። ማቴ ፲፥ ፪ ሉቃ ፰፥ ፲፯ ።

፳፪ የማይገለጥ የተሰወረ የለምና ፥
ወአልቦ ክዱን ዘኢይትከሠት ።
የማይገለጥ የተሸፈነ የለምና ፥

፳፫ ወዘቦ እዝነ ሰሚዓ ሊይስማዕ

፳፫ ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ ።

፳፬ ወይቤሎሙ ለብዉ ዘትሰምዑ ማቴ ፯፥ ፪ ሉቃ ፮፥ ፴፰ ፥

፳፬ የምትሰሙ እናንተ አስተውሉ ፥
በውእቱ መሥፈርት ዘሰፈርክሙ ይሰፍሩ ለክሙ
በሰፈራችሁበት መሥፈሪያ ይሰፍሩላችኋል ።
ወይዌስኩክሙ
ይጨምሩላችኋልም እንደ አእምሯችሁ ሕጸጽ መጠን እንዲመስሉባችሁ ዕወቁ አላቸው ።

፳፭ እስመ ለዘቦ ይሁብዎ

፳፭ ላለው ይሰጡታል
ወይዌስክዎ ። ማቴ ፲፫፥ ፲፪ ሉቃ ፰፥ ፲፰ ፲፱፥ ፳፮ ፤
ይጨምሩለታልና ።
ወለዘሰ አልቦ እለሂ ቦ የሐይድዎ ።
የሌለውን ግን ያለውን ቅሉ ይወስዱበታል ።

በእንተ ዘርዕ መማዕረር ።

፳፮ አኮኑ ከመዝ ርትዕት ይእቲ መንግሥተ ሰማያት ከመ ብእሲ ዘይዘርዕ ሠናየ ዘርዓ ውስተ

፳፯ ገራንቱ ወነዊሞ ይትነሣእ መዓልተ ወሌሊተ ወይዋሕዮ

፳፯ ነዊሞ ሌሊተ ይትነሣእ መዓልተ ብሰሀግጠም ፥ መንግሥተ ሰማይ ሕገ ወንጌል ፥ ሕገ ወንጌል ተስፋ ፥ ተስፋ ኢየሱስ

፳፯ ክርስቶስ በርሻው መልካም ዘር ዘርቶ ሌሊት ተኝቶ ቀን ተነሥቶ እርሻውን የሚጐበኝ ገበሬን ትመስላለች እኮን ፥ ትመስል የለምን ፥ ሐተታ ፥ ጌታ ኑሮ ኑሮ ለበውከሙኑ ማለቱን መናገር ነው ።
ወዘርዑ የዓቢ ወይልሕቅ ፥
ዘሩም በቅሎ ያድጋል ።

፳፰ ወውእቱሰ የአምር ከመ ባሕቲታ ምድር ትሁብ ፍሬሃ ፥

፳፰ እሱም ምድር የዘሩባት እንደሆነ ፍሬ እንድታቀርጥ ዐውቆ ይዘራባታል ፥ እኔም የተማራችሁ እንደሆነ ከፍጹምነት እንድትደርሱ ዐውቄ አስተምራችኋለሁ ። አንድም ውእቱሰ የአምር ከመ ኢትሁብ ምድር ፍሬ ፥ ምድር ካልዘሩባት ፍሬ እንዳታቀርጥ ዐውቆ ይዘራል ። እኔም ካልተማራችሁ ከፍጹምነት እንዳትደርሱ ዐውቄ አስተምራችኋለሁ ፥ አንድም ውእቱሰ ኢየአምር ከመ ትሁብ ወከመ ኢትሁብ ፍሬ ይላል ፥ እሱ ታቀርጥም እንደሆን አታቀርጥም እንደሆን ሳያውቅ ይዘራል ። እኔ ግን የተማራችሁ ያወቃችሁ እንደሆን ፍጹማን እንድትሆኑ ከፍጹምነት እንድትደርሱ አውቄ አስተምራችኋለሁ ።
ቀዳማዊ ሣዕረ ፥
መጀመሪያ ሣዕርን ማለት ቡቃያ ወእምዝ ሰብለ ፥
ቀጥሎ ዝርዝር ወእምሰብል ይመልእ ፍጹመ ሥርናየ በዛላው ሥንዴን ይመላል ማለት ጎምር ይሆናል ።

፳፱ ወሶበ ፈጸመ ፈርየ ይፈኑ ማዕፀደ ።

፳፱ ፈጽሞ ባፈራ ጊዜ ማለት መከር በደረሰ ጊዜ እጁ ይልካል ። አንድም ቡቃያ ጥንተ ስብከት ዝርዝር ቂሣርያ ጎምር ደብረ ታቦር ይፈኑ ማዕፀደ ዕለተ ዓርብ ፥ አንድም ቡቃያ ቂሣርያ፥ ዝርዝር ደብረ ታቦር ፤ ጎምር ዕለተ ዓርብ ይፈኑ ማዕፀደ ትንሣኤ ዕርገት ዕለተ ምጽአት ። አንድም ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና፥ ይፈኑ ማዕፀደ ሞት ሠናይት ነው ።
እስመ በጽሐ ማዕረር ፤
መከር ደርሷልና ።

በእንተ ኅጠተ ሰናፔ ።

፴ ወይቤ በምንት እስተማስላ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ።

፴ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን እመስላታለሁ ።
ወምንተ ትመስል ።
ማንንስ ትመስላለች ።

፴፩ ትመስል ኅጠተ ሰናፔ እንተ ተዘርዓት ውስተ ምድር ማቴ ፲፫፥፴፩ ፥ ሉቃ ፲፫፥፲፰ ።

፴፩ በምድር የተዘራች የሰናፍጭ ቅንጣትን ትመስላለች ።

፴፪ ወእምከመ ተዘርዓት ትበቊል ፥

፴፪ በተዘራችም ጊዜ ትበቅላለች ።
ወተዓቢ እምኵሎን አህማላት ፤

ከሰምስም ሁሉም ትበልጣለች ወትገብር አዕጹቀ
ዓበይተ ታላላቅ ጫፎችም ታወጣለች ። እስከ ይክሉ
አዕዋፈ ሰማይ አጽልሎ ታኅተ አዕጹቂሃ ፤
የሰማይ ወፎች ከጽላዋ በታች ማረፍ እስኪቻላቸው

፴፫ ወበዘከመዝ አምሳል ተናገሮሙ ቃሎ በአ
ምጣነ ይክሉ ሰሚዓ ፤

፴፫ መስማት በሚቻላቸው መጠን እንዲህ
ባለ ምሳሌ ቃሉን ነገራቸው ።

፴፬ ወዘእንበለ ምሳሌሰ ኢተናገሮሙ ።
፴፬ ያለ ምሳሌ ግን አልነገራቸውም ወበባ
ሕቲቶሙ ለአርዳኢሁ ይፈክር ኵሎ ።
ለደቀ መዛሙርቱ ግን ለብቻቸው ሁሉን ይተረጕም
ላቸው ነበር ።

፴፭ ወይእተ ዕለተ ሶበ መስየ ይቤሎሙ ለአ
ርዳኢሁ ንዕዱ ማዕዶተ ።
፴፭ በዚያም ቀን በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙ
ርቱን ወደማዶ እንሂድ አላቸው ።
፴፮ ወኃደጎሙ ለሕዝብ ወነሥእዎ በሐመር
ምስሌሆሙ ። ማቴ ፰፥፳፫ ሉቃ ፰፥፳፪፥ ፴፮ ።
፴፮ ሕዝቡን አሰናብቶ በመርከብ ይዘውት ሄዱ
ወቦ ካልዓትኒ አሕማር ምስሌሆሙ ።
ሌሎችም መርከቦች ከሳቸው ጋራ ነበሩ ።
፴፯ ወመጽአ ዐውሎ ዓቢይ ነፋስ ።
፴፯ ታላቅ ዓውሎ ነፋስ መጣ ወይሰውጥ ማየ
አሞገድ ውስተ ሐመር እስከ ይመልእ ማየ ውስተ
ሐመር ።
ውኃው መርከቡን እስኪመላው ድረስ ውኃውን
እያፈሰ ከመርከቡ ይጨምረው ነበር ።
፴፰ ወውእቱሰ መንገለ ከዋላ ሐመር ከተር
ኢሶኖመ እሱ ግን በከበሮ ቤት በኩል
፴፰ ከንዱን ተንተርሶ ተኝቶ ነበር ።
ወአንቅሕዎ ። ቀሰቀሱት ።
ወይቤልዎ ሊቅ ኢየኃዝነከኑ እንዘ ንመውት ፤
መምህር ሆይ ስንሞት አናሳዝንህም አሉት ።
፴፱ ወተንሥአ ወገሠፆሙ ለነፋሳት
፴፱ ተነሥቶ ነፋሳትን ገሠጻቸው ።
ወይቤላ ለባሕር ተፈጸሚ ወአርምሚ ።
ባሕርን ጸጥ በይ ዝም በይ አላት ወኅደገ ነፋስ ።
ነፋስ መንፈሱን ተወ ።
ወኮነ ዓቢይ ዛኅን ፤
ታላቅ ጸጋታም ተደረገ ፤
፵ ወይቤሎሙ ምንትኑ ያፈርኃከሙ አ
ድኩማን ።
፵ እናንተ ደካሞች ምን ያስፈራችኋል ፤
ከመዝኑ አልብክሙ ሃይማኖት ፤
እንዲህ ሃይማኖት የላችሁምን አላቸው ።
፵፩ ወፈርሁ ዓቢየ ፍርሃተ
፵፩ ፈጽመው ፈሩ ፤

ወተበሀሉ በበይናቲሆሙ መኑ እንጋ ውእቱ ዝንቱ
ዘይትኤዘዙ ሎቱ ባሕርኒ ወነፋሳትኒ ።
ባሕርም ነፋሳትም የሚታዘዙ ለት ይህ ማነው እንጃ
አሉ ።

ምዕራፍ ፭ ።

፩ ወበጺሖሙ ማዕዶተ ባሕር ኀበ ብሔረ
ጌርጌሴኖን ። ማቴ ፰፥፳፰። ሉቃ ፰፥፳፮ ።

፩ በባሕር ማዶ ወዳለ ወደ ጌርጌሴኖን ደረሱ።
፪ ወወሪዶ እምሐመር ተቀበሎ ሶቤሃ ብእሲ
ዘአኩይ ጋኔን ላዕሌሁ ወጺአ እመቃብር ፤

፪ ከመርከቡ በወረደ ጊዜ ርኩስ ጋኔን የያዘው
ሰው ከመቃብር ወጥቶ ተገናኘው ።

፫ ወይነብር ውስተ መቃብር
፫ ከመቃብር ይኖር ነበር ።
ወሰዕንዎ አውዕአቶ በመዋቅሕትኒ እንዘ ዘልፈ
ይሞቅሕዎ ዘወትር ሲያስሩት በሰንሰለት ሰንኳ ማጽ
ናት ተሳናቸው ።
ወአልቦ ዘይክል አድክሞቶ ።
የሚችለው አልነበረም ።

፬ እስመ መዋቅሕተኒ ይሰብር
፬ እግር ብረቱንም ይሰብረው ነበርና ።
ወሰናስሉኒ ይቀጠቅጥ ።
ሰንሰለቱንም ያወልቅ ነበረና ።
ወያዓቅብዎ ደቅ
ሕፃናት ይጠብቁት ነበርና ሐተታ፥ ግብረ አበር
ናቸውና ብር ብር እያሉ አንድም ኃያል ሲል ነው
ለይትነሥኡ ደቅን ወይትዋነዩ በቅድሜነ እንዲል

፭ ወዘልፈ የዓወዩ መዓልተ ወሌሊተ በው
ስተ መቃብር ወበውስተ አድባር ፤

፭ ሁልጊዜም በመዓልትና በሌሊት በመቃብ
ርና በተራራ ይጮህ ነበረ ።
ወይጌምድ ሥጋሁ በእብን
ሥጋውንም በድንጊያ ይፈጨው ነበር
፮ ወሶበ ርእዮ ለእግዚእ ኢየሱስ እምርኁቅ
ሮፀ ወሰገደ ሎቱ ፤
፮ ጌታን በሩቅ ባየው ጊዜ መጥቶ ሰገደለት።
፯ ወጸርሐ በዓቢይ ቃል ወይቤ ምንት ብየ
ምስሌከ ኢየሱስ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ፤
፯ የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ
ካንተ ጋራ ምን ጠብ አለኝ ።
አምሕለከ በእግዚአብሔር ሕያው ከመ ኢትማቅየኒ
እንዳታሰቃየኝ በሕያው በእግዚአብሔር አምልሐለሁ
ብሎ በታላቅ ቃል አሰምቶ ተናገረ ።
፰ እስመ ይቤሎ ለውእቱ ጋኔን እኩይ ፃእ
እምላዕሌሁ ።
፰ ያን ርኩስ ጋኔን ውጣ ይለው ነበርና ።

፱ ወተስእሎ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ መኑ ስምከ ፧

፱ ኢየሱስም ስምህ ማነው ብሎ ጠየቀው ። ወይቤሎ ውእቱ ጋኔን ሌጌዎን ስምየ እስመ ብዙኃን ንሕነ ፤ ያም ጋኔን ብዙ ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው አለ ። ሐተታ ቁጡ ማለት ነው ዘበእንተ መዓቶሙ ተሰምዩ ሌጌዎነ እንዲል ።

፲ ወአስተብቍዖ ብዙኃ ከመ ኢይሰድዶ እፍአ እም ብሔር ።

፲ ካገር ወደውጭ እንዳይሰዳቸው መላልሶ ለመነው ።

፲፩ ወቦ ህየ መራዕየ አኅርው ብዙኃ ይትረዓይ መንገለ ደብር ፤

፲፩ ከዚያ ብዙ የሪያ መንጋ በተራራ አጠገብ ተሰማርቶ ነበር ።

፲፪ ወአስተብቍዕዎ ብዙኃ እሉ አጋንንት ወይቤልዎ እመ ታወጽአነ ፈንወነ ውስተ አኅርው ከመ ንባዕ ላዕሌሆሙ ።

፲፪ በእሪያዎች እንገባባቸው ዘንድ አሰናብተን ብለው ለመኑት ።

፲፫ ወአብሖሙ እግዚእ ኢየሱስ
፲፫ ጌታም ፈቀደላቸው ።
ወወፂኦሙ እሙንቱ አጋንንት ቦኡ ላዕለ አኅርው
እኒያም አጋንንት ከሰዎቹ ወጥተው በእሪያዎች ገቡ
ወዓብዱ እሙንቱ መራዕይ ወፀድፉ ውስተ ባሕር
የሪያውም መንጋ ሁሉ ሮጠው ከባሕር ወደቁ ።
ወኮኑ መጠነ ፳፻
ሁለት ሺህ ያህሉ ነበር
ወሞቱ ውስተ ባሕር
በባሕርም ውስጥ ሞቱ ።

፲፬ ወጕዩ ኖሎት ወዜነው ለአኅጕር ወለአዕጻዳት
፲፬ እሪያ ጠባቆች ግን ሸሽተው በአደባባይና በሀገሩ አወሩ ፤
ወወጽኡ ይርአዩ ዘኮነ ፤
የሆነውንም ለማየት ወጡ

፲፭ ወርእዩ ወመጽኡ ኀበ እግዚእ ወረከብዎ ለዘጋኔን አኀዞ እንዘ ይነብር ድኅነ ወልቡሂ ገቢኦ ወልቡሰ ልብሰ ዝኩ ዘአኀዞ ሌጌዎን ።

፲፭ ወደጌታም በመጡ ጊዜ ያ ጋኔን ያደረበትን ሰው አእምሮው ተመልሶ ልብሱን ለብሶ ከጌታ ጋራ ተቀምጦ አገኙት ሐተታ ማቴዎስ ሁለት ሰዎች ናቸው ይላል፤ማርቆስ አንድ ሰው አለ እንደም ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ሁለት ናቸው ማርቆስ አንድ ማለቱ ለመንገር ከበቃ ብሎ አንድም አንዱ የፀናበት አንዱ ያልፀናበት ነው ማቴዎስ የጸናበትንም ያልጸናበትንም ቆጥሮ ሁለት አለ ማርቆስ ያልጠናበትን ትቶ አንድ አለ ፧
ወፈርሁ ፤
ፈሩ ።

፲፮ ወዜነውዎሙ እለ ርእዩ ዘከመ ኮነ ዘጋኔን ወዘበእንተ አኅርው ፤

፲፮ ጋኔን ያደረበት ሰው የሆነውን በእሪያዎችም የተደረገውን ያዩ ሰዎች ነገሩዋቸው ፤

፲፯ ወአኀዙ ያስተብቍዕዎ ከመ ይፃዕ እምደወሎሙ ።

፲፯ ካገራቸው ይሄድ ዘንድ ይለምኑት ጀመሩ፤

፲፰ ወዓሪጎ ሐመረ ወአስተብቍዖ ውእቱ ዘጋኔን ይሑር ምስሌሁ ፤

፲፰ ከመርከብ በወጣ ጊዜም ያ ጋኔን ያደረበት ሰው ከሱ ጋራ ይሄድ ዘንድ ማለደው ። ሐተታ ምናኔ ሽቶ ይመሰሰብኛል ብሎ ፈርቶ ፤

፲፱ ወከልኦ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ሑር ውኢቱ ቤተከ ኀበ አሊአከ ።

፲፱ ጌታ ከለከለው ምናኔ ሽቶ ላለው አማህ ምናኔ አይደለም ወደቤትህ ወደወገኖችህ ሂድ አለው።
ወንግር ኵሎ ዘገብረ ለከ እግዚአብሔር
እግዚአብሔር ያደረገልህን አተስምር አለው ።ሐተታ ይመሰስብኛል ብሎ ፈርቶ ላለው እይዞህ አይመለስብህም ከቤትህ ሂደህ እግዚአብሔር ያደረገልህን ተአምራት አስተምር አለው ወዘከመ ተሣሃለከ ይቅርም እንዳለህ ተናገር ፧

፳ ወሖረ ወአኃዘ ይስብክ በዐሥሩ አኅጕር ኵሎ ዘገብረ ሎቱ ኢየሱስ ።

፳ ጌታ ያደረገለትን ሁሉ ባሥሩ አገር ያስተምር ጀመረ ።
ወአንከሩ ኵሎሙ
ሁሉም አደነቁ ።
ዘከመ ፈወሶን ለአንተ ደም ይውኅዛ ወለወለተ ኢያኢሮስ ።

፳፩ ወካዕበ ዓደወ እግዚእ ኢየሱስ በሐመር ማዕዶተ ።

፳፩ ዳግመኛም ጌታ በመርከብ ወደማዶ ተሻገረ ወተጋብኡ ብዙኃን ሰብእ ኀቤሁ ኀበ ሐይቀ ባሕር በባሕር አጠገብ ሳለ ብዙ ሰዎች ወደሱ ተሰበሰቡ

፳፪ ወመጽአ ኀቤሁ ፩ዱ ብእሲ መጋቤ ምኵራብ ዘስሙ ኢያኢሮስ

፳፪ የምኵራብ ሹም ኢያኢሮስ የሚባል አንድ ሰው ወደሱ መጣ ወሰበ ርእዮ ሰገደ ሎቱ ታሕተ እገሪሁ ፤ ባየውም ጊዜ ከእግሩ በታች ሰገደለት

፳፫ ወብዙኃ አስተብቍዖ
፳፫ እጅግም ለመነው ።
ወይቤ ወለትየ እልጽቀት ትሙት
ልጄ ልትሞት ቀርባለች
ወባሕቱ ነዓ ደይ እደከ ላዕሌሃ ወተሐዩ
ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት ትድናለች ።

፳፬ ወሖረ እግዚእ ኢየሱስ ምስሌሁ ወተለውዎ ብዙኃን ሰብእ ፤

፳፬ ብዙ ሰው ተከተሉት ከሱ ጋራ ሔደ ፤
ወተጋፍዕዎ
ያጫንቁት ነበር ።

፳፭ ወመጽእት ብእሲት እንተ ደም ይውኅዛ እምነ ፲ቱ ወ፪ቱ ክረምት

፳፭ ካሥራሁለት ዓመት ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት መጣች ።

፳፮ ወብዙኃ አሕመምዋ ብዙኃን ዓቀብተ ሰራይ እንዘ ይፌውስዋ ።

፳፮ እናድናታለን እያሉ ብዙ ባለመድኃኒቶች ብዙ አደከሟት ።
ወአስተዋጽአት ኵሎ ንዋያ ወአኀለቀት ።
ገንዘቧን ሁሉ አውጥታ ጨረሰች
ወአልቦ ዘበቍዓ ዘእንበለ ዳዕሙ ዘአልህማ
እየጸናባት ከመሄድ በቀር የረባት የጠቀማት የለም ሰብእ ጥቀ እኩይ ውእቱ ወአርዌ ምድር ይልሕም እከየ እንዲል ። ዘእንበለ ዘብእሳ ዘእንበለ ዘተወሰከ ሕማም ይላል እየባሰባት እየታከለባት ከመሄድ በቀር የጠቀማት የለም ።

፳፯ ወሰሚዓ በእንተ እግዚእ ኢየሱስ መጽአት ወቦአት ማዕከለ ሰብእ ወገሠሠት ጽንፈ ልብሱ እንተ ድኅሬሁ ።

፳፯ የጌታን ነገር በሰማች ጊዜ መጥታ ከሰው መካከል ገብታ በኋላ የልብሱን ዘርፍ ዳሰሰች

፳፰ እንዘ ትብል እምከመ ገሠሥኩ ጽንፈ ልብሱ አሐዩ እምደዌየ ።

፳፰ የልብሱን ዘርፍ የያዝኩ እንደሆነ እድናለሁ ብላ ፣

፳፱ ወሶቤሃ ነጽፈ ነቅዓ ደማ ፣

፳፱ ያን ጊዜውንም የደሟ ምንጭ ደረቀ ።
ወአንከረት ርእሳ ወሐይወት እምደዌሃ
ከደዌዋ እንደዳነች እሷ አደነቀች ። አንድም ወአእመረት ርእሳ ፣ ጥዒና ተሰማት ።

፴ ወአእመረ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ወፅአ ኃይል እምኔሁ ወተመይጠ ኀበ ሰብእ ይቤሎሙ መኑ ገሠሠኒ ጽንፈ ልብስየ

፴ ጌታም ኃይል ከሱ እንደወጣ ዐውቆ ወደ ሰዎቹ ተመልሶ የልብሴን ዘርፍ የያዘኝ ማነው አላቸው

፴፩ ወይቤልዎ አርዳኢሁ ኢትሬኢኑ ሰብእ እንዘ ይትጋፍዑከ እንተ ትብል መኑ ገሠሠኒ ጽንፈ ልብስየ ።

፴፩ ደቀ መዛሙርቱ ሰው ሲያጫንቅህ አታይምን የልብሴን ዘርፍ ማን ዳሠሠኝ ትላለህ አሉት

፴፪ ወተመይጠ ከመ ይርአይ ዘገብረ ዘንተ

፴፪ ይህን ያደረገን ሊያይ ተመለሰ

፴፫ ወፈርሃት ይእቲ ብእሲት

፴፫ ያች ሴት ፈራች
ወርእደት ጥቀ
እጅግ ተጨነቀች
እስመ አእመረት ዘኮነ ላዕሌሃ
የተደረገባትን ስላወቀች
ወመጽአት ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወሰገደት ሎቱ ታሕተ እገሪሁ
ወደ ጌታ መጥታ ሰገደችለት ወነገሮ ኵሎ ጽድቀ
እውነቱንም ሁሉ ነገረችው

፴፬ ወይቤላ ወለትየ ሃይማኖትኪ አሕየወተኪ እትዊ በሰላም ።

፴፬ ልጄ ሃይማኖትሽ አድኖሻልና በደህና ሂጅ አላት ።
ወሕየዊ እምደዌኪ
ከደዌሽም ተፈወሽ አላት

፴፭ ወእንዘ ይትናገር ምስሌሃ መጽኡ ምስሌሃ ኀበ መጋቤ ምኵራብ ወይቤልዎ ወለትከሰ ሞተት ወኢታፃምዎ እንከ ለሊቅ ።

፴፭ ከሷ ጋራ ሲናገር ሰዎች ወደሹሙ መጥተው ልጅህስ ሞታለች ከአንግዲህስ ወዲህ መምርን እታድክመው አሉት ። ሐተታ ማቴዎስ ወለትየ ሞተት አለው ይላል ። ማርቆስ አልጸቀት ትሙት አለው አለ ፣ እንደምነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ወለትየ ሞተት ብሎታል ሞተች አልክ ቢለው ደንግጦ አልጸቀት ትሙት ብሎታል እንደ ማርቆስ ይህን ተከፍሎው ጽፈዋል ። አንድም ነገር እንደ ማርቆስ ነው እልፀቀት ትሙት ብሎታል ዝግጥግጥ ቢልበት ፈጥኖ ይሄድልኛል ብሎ ወለትየ ሞተት ይለዋል ይህን ተከፍለው ጽፈዋል ። አንድም አልጸቀት ትሙት ብሎታል ብላቴኖች መጥተው ወለትከሰ ሞተት ኢታፃምዎ እንከ ለሊቅ አሉት የብላቴኖቹን ቃል ይዞ ሞተት ብሎታል የፊተኛውን ማርቆስ የኋለኛውን ማቴዎስ ጽፉ ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ።

፴፮ ወሰሚዖ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይትናገርዎ ይቤሎ ለመጋቤ ምኵራብ ኢትፍራህ ተአመን ዳዕሙ ተሐዩ ወለትከ ።

፴፮ ጌታ ግን ሲነግሩት ሰምቶ የምኩራቡን ሹም እመን እንጂ አትፍራ ልጅህም ትድናለች አለው

፴፯ ወከልዓ ከመ እልቦ ዘይተልዎ ዘእንበለ ጴጥሮስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ እኁሁ ለያዕቆብ ።

፴፯ ከያዕቆብ ከጴጥሮስ ከያዕቆብ ወንድም ከዮሐንስም በቀር የሚከተለው እንዳይኖር ከለከለ

፴፰ ወቦአ ቤቶ ለመጋቤ ምኵራብ

፴፰ ከምኩራብ ሹም ቤት ገባ ።

ወረከቦሙ እንዘ ይትሐወኩ ወይበክዩ ወየአወይዉ ብዙኃ ሲያለቅሱና ሲታወኩ በብዙም ሲጮሁ አገኛቸው ።

፴፱ ወቦአ ወይቤሎሙ ለምንት ትትሐወኩ፤
፴፱ ገብቶ ለምን ትታወካላችሁ አላቸው ።
ወትበክዩ
ለምን ታለቅሳላችሁ
ሕፃን ኢሞተት
ብላቴናይቱስ አልሞተችም አላቸው
አላ ትነውም ።
ተኝታለች እንጂ አላቸው ።

፵ ወሰሐቅዎ   ሳቁበት
፵ ወአውፅአ ለኵሉ ወነሥኦሙ ለአቡሃ ወለእማ ለሕፃን ወእለ ምስሌሁ ወቦአ ኀበ ሀለወት ሕፃን ።
[illegible] በኋላ ሁሉን አስወጥቶ የብላቴናይቱን እናትና አባት ከእርሱም ጋራ የነበሩትን ይዞ ብላቴናይቱ ካለችበት ገባ ።

፵፩ ወአኀዛ እዴሃ ለሕፃን ፤
፵፩ የብላቴናይቱን እጁዋን ያዛት
ወይቤላ ጣቢታ ቁሚ
ጣቢታ ቁሚ አላት ፤
ተንሥኢ ወለትየ ብሂል በትርጓሜሁ ።   ትርጓሜው ልጄ ተነሽ ማለት ነው ።

፵፪ ወተንሥአት ሶቤሃ ይእቲ ወለት ወአንሶሰወት ።

፵፪ ያችም ብላቴና ፈጥና ተነሥታ ሄደች ።
ወ፲ቱ ወ፪ቱ ክረምታ
ዐሥራ ሁለት ዓመት ሁኑዋት ነበር ።
ወደንገጹ ሶቤሃ ዓቢየ ድንጋጼ
ያን ጊዜም ታላቅ ድንጋጤ ደነገጡ ።

፵፫ ወገሠጾሙ ለአቡሃ ወለእማ ብዙኃ ከመ አልቦ ዘየአምር ዘንተ

፵፫ ይህን ማንም ማን የሚያውቀው እንዳይኖር እናት አባቷን ብዙ ገሠጻቸው ።
ወአዘዘ የሀብዋ ዘትበልዕ
የምትበላውም ስጧት አለ ።

በከመ ሰበከ ኢየሱስ በናዝሬት

ምዕራፍ ፮ ።

፩ ወወፅአ እግዚእ ኢየሱስ እምህየ ቦአ ሀገረ። ማቴ ፲፫፥፶፬ ሉቃ ፬፥፲፮ ።

፩ ከዚያም ወጥቶ ወደ ሀገሩ ገባ
ወተለውዎ አርዳኢሁ
ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት ።

፪ ወበሰንበት መሐሮሙ በምኵራብ
፪ ቅዳሜ በምኵራብ አስተማራቸው ።
ወብዙኃን ያጸምዕዎ ወያነክሩ እንዘ ይብሉ እምአይቴ ሎቱ ዝንቱ ኵሉ ትምህርት ።
ብዙ ሰዎች ሰምተው ይህ ሁሉ ከወዴት ተገኘለት ብለው አደነቁ ።
ወምንትኑ ዛቲ ጥበብ እንተ ተውህበት ሎቱ
ይህችስ የተሰጠችው ጥበብ ምንድናት ።   ወዝኒ
ኃይል ዘይትገበር በእደዊሁ ።
ይህስ በእጁ የሚደረግ ኃይል ምንድን ነው ።

፫ አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለፀራቢ ዮሐ ፮፡ ፵፪ ።

፫ የፀራቢ ልጅ አይደለምን
ወወልደ ማርያም
የማርያምስ ልጅ አይደለምን ።
ወእኁዊሁኒ ያዕቆብ ወዮሳ ወይሁዳ ወስምዖን ፤
ወንድሞቹስ ዮሳና ያዕቆብ ይሁዳም ስምዖንም አይደሉምን ።   ወአኮኑ አኃቲሁኒ ሀለዋ ዝየ ኀቤነ
እኅቶቹስ ከኛ ዘንድ ያሉ አይደለምን ብለው ።
ወተአቅፉ ።
በሱ ምክንያት ተጠራጠሩ ።

፬ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አኮኑ ምኑን ነቢይ ዘእንበለ በሀገሩ ወበቤቱ ወበኀበ አዝማዲሁ ማቴ ፲፫፥፶፯ ። ሉቃ ፬፥፳፬ ። ዮሐ ፬፥፵፬ ።

፬ ጌታም ነቢይ በሀገሩና በወገኑ በቤቱም በቀር አይናቅም አላቸው ።

፭ ወኢገብረ ኃይለ በህየ ዘእንበለ ኅዳጣን ድውያን ዘአንበረ እዴሁ ዲቤሆሙ ወአሕየዎሙ

፭ እጁን ጭኖ ካዳናቸው ከጥቂት በሽተኞች በቀር በዚያ ኃይል ተአምራት አላደረገም።

፮ ወአንከረ ኢአሚኖቶሙ ።
፮ አለማመናቸውን አደነቀ
ወአንሶሰወ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ኵሉ አህጉረ አድያም እንዘ ይሜህር ።
እያስተማረ በአውራጃው ሀገር ሁሉ ተመላለሰ ።

ዘከመ ፈነዎሙ ለሐዋርያት ይስብኩ ።

፯ ወጸውዖሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ሐዋርያት ። ማቴ ፲ ፥ ፩ ። ማር ፫ ፥ ፲፬ ። ሉቃ ፱ ፥ ፩ ።

፯ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጣቸው ።
ወፈነዎሙ ፪በ፪ቱ ሁለት ሁለቱን ላካቸው ሐተታ አንዱ ቢደክም አንዱ ያጸናዋልና ለእመ ወድቀ ፩ዱ ያነሥኦ ካልዑ ፈትል ሥሉስ ኢይትበተክ እኁኒ ዘይትራዳእ እኅዋሁ ከመ ሀገር እንተ ባቲ ጥቅም እንዲል ።   ወአብሆሙ ላዕለ አጋንንት እኩያን በከፉ አጋንንት ላይ ሥልጣን ሰጣቸው ።

፰ ወኢዘዘሙ ከመ አልቦ ዘይስነቁ ለፍኖት
፰ ለመንገድም ስንቅ እንዳይዙ አዘዛቸው ።
ወኢይንሥኡ ዘእንበለ በትር ባሕቲታ ።
ከበትር ብቻ በቀር እንዳይዙ ሐተታ፡ ማቴዎስ ኢበትረ ይላል ፥ ከዚህ ማርቆስ ዘእንበለ በትር አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም አምልኮቱን እስኪያውቁ ድረስ አትያዙ ይላል አምልኮቱን ካወቁ በኋላ ግን ቢይዙም ባይዙም አይጎዳምና ዘእንበለ በትር አለ አንድም ማቴዎስ ጌጸኛውን አትያዙ ሲል ኢበትረ አለ ። ማርቆስ ቀራውን ሲል ነው ። አንድም በትር ሳይቀር አትያዙ ሲል ነው ። ወኢኅብስተ ።
እንጀራ ስንኳ ።
ወኢጽፍነተ ።
ከረጢትም ። ኢወርቀ
ወኢብሩረ ።
ወርቅ ብር አትያዙ ።
ወኢጸሪቀ ውስተ ቅናቶሙ ።
በመታጠቂያቸውም ናስ ፤

፱ ዘእንበለ አሣዕን ዘውስተ አገሪሆሙ ። ግብ ፲፪ ፥ ፰ ።

፱ በእግራቸው ካለ ጫማ በቀር ፤
ሐተታ ፥ ማቴዎስ ኢአሣዕነ ይላል ከዚህ ማርቆስ ዘእንበለ አሣዕን አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም አምልኮቱን እስኪያውቁ ድረስ አታድርጉ ይላል አምልኮቱን ካወቁ በኋላ ግን ቢያደርጉትም ባያደርጉትም አይጎዳምና ዘእንበለ አሣዕን አለ አንድም ማቴዎስ ጌጸኛውን ሲል ነው ፤ አንድም ጫማ ሳይቀር አታድርጉ ሲል ነው አግብኡ ሊተ ንዋይየ ዘእንበለ ብእሲትየ እንዲል ። ወኢይልበሱ ፪ኤ ክዳናተ ሁለት ልብስም እንዳይለብሱ ፤

፲ ወይቤሎሙ ቤተ ኀበ ቦእክሙ ሀየ ንበሩ እስከ አመ ትወጽኡ እምሀየ ።

፲ ከዚያ እስክትወጡ ድረስ በገባችሁበት ቤት ኑሩ ።

፲፩ ወብሔረ ኀበ ኢተወከፉክሙ ወኢሰምዑክሙ ወኢአክሙ እምሀየ ንግፋ ፀበለ አገሪክሙ ማቴ ፲፥፲፬፥ ሉቃ ፱፥፭ ፥ ግብ ፲፫፥፶፩ ።

፲፩ የማይሰሟችሁና የማይቀበሏችሁ ሰዎች ካሉበት ሀገር ወጥታችሁ የግራችሁን ትቢያ አራግፉ ከመ ይኩን ስምዓ ላዕሌሆሙ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ ።
አማን እብለክሙ ከመ ይረክባ ሳሕተ ሰዶም ወገሞራ አመ ዕለተ ደይን እምይእቲ ሀገር ።
ከዚያች አገር ይልቅ ሰዶም ገሞራ በፍርድ ቀን ዕረፍትን እንዲያገኙ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፲፪ ወወፂኦሙ ሰበኩ ከለሄ ከመ ኰሉ ይኔሥሑ
፲፪ በወጡም ጊዜ ሁሉ ንስሐ ይገቡ ዘንድ አስተማሩ ።

፲፫ ወብዙኃነ አጋንንተ ያወጽኡ ፤
፲፫ ብዙ አጋንንትም ያወጡ ነበር
ወይቀብዕዎሙ ቅብዓ ለብዙኃን ድውያን ። ያዕ ፭፥፲፬ ።
ብዙ በሽተኞችንም ዘይት ይቀቧቸው ነበር ።
ወየሐይዉ
ይድኑም ነበር ፥ ሐተታ መጽሐፈ ቀንዲል የሚባል አለ ያን በዘይት እየደገሙ ይቀቧቸው ነበርና ። አንድም ጸሎቱን ቅብዕ አለው ሌላውን የሚቀባው ሰው እጁን ሳይነካው እንዳይቀር ጸሎትም የሚጸልይ ሰው ራሱን ሳይጠቅም ሌላውን አይጠቅምምና

ዘከመ ሰምዓ ኮነ ዮሐንስ መጥምቅ ።

፲፬ ወሰሚዖ ሄሮድስ ንጉሥ እስመ ከሠተ ኮነ ስሙ ወይቤ ዮሐንስ መጥምቅ ተንሥአ እምነ ምውታን ማር ፲፬፥፪ ሉቃ ፱፥፯ ።

፲፬ ሄሮድስ ንጉሥ ስሙ እንደተገለጠ ሰምቶ ዮሐንስ መጥምቅ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል ። ወበእንተዝ ይትገበር ሎቱ ኃይል ስለዚህ ኃይል ይደረግለታል ይረዳዋል አለ ።

፲፭ ወቦ እለ ይቤሉ ኤልያስ ውእቱ
፲፭ ኤልያስ ነው ያሉም አሉ ። ወቦ እለ ይቤሉ ነቢይ ውእቱ ነቢይ ነው ያሉም አሉ ።
ወእመ አኮ ከመ ፩ዱ እምነቢያት ። ወይም ከነቢያት አንዱ ነው አሉ ።

፲፮ ወሰሚዖ ሄሮድስ ይቤ ዮሐንስ ውእቱ ዘአነ መተርኩ ርእሶ ።

፲፮ ሄሮድስ ግን በሰማ ጊዜ እኔ እራሱን የቈረጥኩት ዮሐንስ ነው አለ ።
ውእቱ ተንሥአ እሙታን
እሱ ከሙታን ተነሥቷል።
፲፯ እስመ ውእቱ ሄሮድስ ፈነወ አግብርቲሁ ወአኃዞ ለዮሐንስ ወሞቅሖ ። ሉቃ ፫፥፲፱ ።
፲፯ እሱ ሄሮድስ ብላቴኖቹን ልኮ ዮሐንስንም ይዞ በግዞት አኑሮት ነበርና ።
በእንተ ሄሮድያዳ ብእሲተ ፊልጶስ እኁሁ ።
በወንድሙ በፊልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት
፲፰ እስመ ኪያሃ አውሰበ እስመ ይቤሎ ዮሐንስ ኢይደልወከ ታውስብ ብእሲተ እኁከ ። ዘሌ ፲፰፥፲፮።
፲፰ እሷን ስላገባ ዮሐንስ የወንድምህን ሚስት ልታገባ አይገባህም ይለው ነበርና ።
፲፱ ወተቀየመቶ ሄሮድያዳ ።
፲፱ ሄሮድያዳም ቂም ይዛበት ነበርና ።
ወፈቀደት ታቅትሎ ።

ሊታስገድለውም ትወድ ነበር ።
ወስዕነት ።
አልተቻላትም ማለት ነውር አጣችበት ።

፳ እስመ ኮነ ይፈርሆ ሄሮድስ ለዮሐንስ ።
፳ ሄሮድስ ዮሐንስን ይፈራው ነበርና ።

እስመ የአምር ከመ ብእሲ ጻድቅ ወቅዱስ ውእቱ
ደግ ሰው ቅዱስም እንደሆነ ስላወቀ ።
ወይትዓቀቦ
ይጠባበቀው ነበር
ወብዙኃ ሰምዖ በኀቤሁ
በሱ ዘንድ ብዙ ነገር ሰምቶ
ወይፈቅድ ይርአይ ተአምረ ዘይገብር
የሚያደርገውን ተአምራት ሊያይ ይወድ ነበር
ወያስተሐውዞ
[illegible] ነበር
ወይፈቅድ ይስምዖ
ሊሰማውም ይወድ ነበር ።

፳፩ ወኮነት ዕለተ እመ ይገብር ሄሮድስ በዓለ በዕለተ ተወልደ ።

፳፩ ሄሮድስ የተወለደበትን በዓል አድርጎ በነበረ ጊዜ
አምሲሐ መኳንንቲሁ
መኳንንቱ ቀኛዝማች ግራዝማቹ ።
ወመላእክቲሁ
አለቆቹን
ወመሳፍንቲሁ
ደጃዝማቾቹን
[illegible]
ሹማምንቱን
ወአበይተ ሀገረ ገሊላ ።
የገሊላን ታላላቆችን ማለት ወይዛዝሩን ምሳ አበላ ።

፳፪ ወቦአት ወለተ ሄሮድያዳ ወዘፈነት
፳፪ ወለተ ሄሮድያዳ ገብታ ዘፈነች
ወአሥመረቶ ለሄሮድስ
ሄሮድስን ደስ አሰኘችው
ወለእለ ይረፍቁ ምስሌሁ
ከሱ ጋራ የተቀመጡትን ደስ አሰኘች ።
[illegible] ንጉሥ ለይእቲ ወለት ሰአልኒ ዘትፈቅዲ
[illegible] ንጉሥም ያችን ብላቴና የምትወጅውን
[illegible] አላት ።

፳፫ ወመሐለ ላቲ ከመ የሀባ ዘሰአለቶ እስከ መንፈቀ መንግሥቱ ።

፳፫ እስከ መንግሥቱ እኩሌታ ስለን የከመ [illegible] ዘንድ ማለላት ።
[illegible] ።
፳፬ ወወፅአት ወትቤላ ለእማ ምንተ እስእሎ
፳፬ ወጥታም እናቷን ምን ልለምነው አለቻት
ወትቤላ ርእሶ ለዮሐንስ መጥምቅ
የዮሐንስ መጥምቅን ራስ አለቻት ።

፳፭ ወቦአት ሶቤሃ ኀበ ንጉሥ እንዘ ትጔጕእ ወሰአለቶ ።

፳፭ ያን ጊዜውንም ፈጥና ወደ ንጉሡ ገብታ ለመነችው ።
ወትቤሎ እፈቅድ ይእዜ ተሀበኒ ርእሶ ለዮሐንስ መጥምቅ ። የዮሐንስ መጥምቅንም ራስ በገበታ አሁን ትሰጠኝ ዘንድ እለምንሃለሁ አለችው ።

፳፮ ወተከዘ ንጉሥ በእንተ መሐላሁ
፳፮ ንጉሥ ስለ ማላው አዘነ ።
ወበእንተዝ እለ ይረፍቁ ምስሌሁ ።
ከሱ ጋራ ስለ ተቀመጡት
ወኢፈቀደ ይዕኀያ
ሊነሳት ግን አልወደደም ።

፳፯ ወፈነወ ንጉሥ ሶቤሃ መስተራትዐተ ሐራ
፳፯ የዚያን ጊዜም ንጉሡ ጭፍራውን የሚያቅናኑትን ላከ
ወአዘዘ ያምጽኡ ርእሶ ፡
ራሱን ያመጡ ዘንድ አዘዘ ፡

፳፰ ወሖሩ ወመተሩ ርእሶ ለዮሐንስ መጥምቅ በቤተ ሞቅሕ ።

፳፰ ሂደው በግዞት ቤት ራሱን ቆረጡ
ወአምጽኡ ርእሶ በፃሕል ወሀብዋ ለይእቲ ወለት
ራሱንም በገበታ አምጥተው ለዚያች ብላቴና ሰጧት
ወይእቲኒ ወለት ወሀበት ለእማ ያችም ብላቴና ለናቷ ሰጠች ።
፳፱ ወሰሚዖሙ አርዳኢሁ ሖሩ ወነሥኡ በድኖ ወቀበርዎ
፳፱ ደቀ መዛሙርቱ በሰሙ ጊዜ ሄደው በድኑን አንስተው ቀበሩት

ዘከመ ተመይጡ ሐዋርያት ።

፴ ወተጋብኡ ሐዋርያት ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወነገርዎ ኵሎ ዘገብሩ ።
፴ ሐዋርያት ወደ ጌታ ተሰብስበው ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት ወዘከመ መሐሩ ።
እንዳስተማሩም ነገሩት
፴፩ ወይቤሎሙ ንዑ ንፃዕ ገዳመ ባሕቲትነ ወታዕርፉ ሕቀ ። ማቴ· ፲፬ ፤ ፲፫ ። ሉቃ· ፱ ፤ ፲ ። ዮሐ· ፮ ፤ ፩ ።
፴፩ ጥቂትም ታርፉ ዘንድ ኑ ለብቻችን ወደ ምድረ በዳ እንሂድ አላቸው ።
፴፪ እስመ ብዙኃን እለ የሐውሩ ወይገብኡ
፴፪ የሚወጡ የሚገቡ ብዙ ነበሩና
ወኢያበውሕዎሙ ይብልዑ እክለ ፡
እህል ይበሉ ዘንድ አያሰናብቷቸውም ነበርና ።

እስመ ኢያስተርከቡ
ጊዜም አሳገኙምና

፴፪ ወሐሩ ሐቅለ በሐመር ባሕቲቶሙ
፴፪ ብቻቸውንም በመርከብ ወደምድረ በዳ ሄዱ ።
ወርእይዎሙ እንዘ የሐውሩ ወአእመርዎሙ ብዙኃን
ብዙ ሰዎችም ሲሄዱ አይተዋቸው ዐወቋቸው
ወሐሩ እንተ እግር ኀቤሁ እምኵሉ አኅጉር
ከየሀገሩ ወጥተው በእግር ወደሱ ሄዱ ።
ወቀዳደምዎሙ ወመጽኡ ኀቤሁ ፡
ቀድመዋቸውም ወደሱ መጡ ።

ዘከመ አብዝኃ በቀዳሚ ኀምስ ኅብስተ

፴፬ ወወፂኦ እግዚእ ኢየሱስ ርእየ ብዙኃ ሰብአ ማቴ. ፱ ፡ ፴፮ ፡ ፲፬ ፡ ፴ ።

፴፬ ጌታም በወጣ ጊዜ ብዙ ሰው አየ ።
ወመሐሮሙ
አስተማራቸውም
እስመ ከመ አባግዕ ዘአልቦ ኖላዊ እሙንቱ
ጠባቂ እንደሌላቸው ሊ.ባግዕ ናቸውና
ወአኃዘ ይምሐሮሙ ብዙኃ
ብዙ ያስተምራቸው ጀመር ።

፴፭ ወእምድኅረ ብዙኅ ሰዓት መጽኡ አርዳኢሁ ወይቤልዎ ሐቅል ውእቱ ዝ ብሔር

፴፭ ከጥቂት ሰዓት በኋላም ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ይህ ቦታ ምድረ በዳ ነው ።
ወሰዓቱኒ ወድዓ መሰየ ።
ጊዜው ፈጽሞ መሸቷል ።

፴፮ ሠዓር ሰብአ ይሑሩ ውስተ አዕፃዳት ወይ ሣየጡ ሎሙ ሲሳየ ። ሉቃ. ፱ ፡ ፲፪ ።

፴፮ ወደ መንደር ሄደው ምግባቸውን ይገዙ ዘንድ ሕዝቡን አሰናብታቸው አሉ ሐተታ ወምቤተ ክዊና እንደ ማቴዎስ ወእምድኅረ ብዙኅ ሰዓት እንደ ማርቆስ ወተቈልቈለ ፀሐይ እንደ ሉቃስ መገናኛ ዮሐንስ በተገናኝ ሲመሽ ማለት ነው ፍትሐሙ ማቴዎስ ሠዓር ሰብአ ማርቆስ ፈንዎሙ ሉቃስ መገናኛ ዮሐንስ በተገናኝ አሰናብት አሉት ።
፴፯ እስመ አልቦሙ ዘይበልዑ
፴፯ የሚበሉት የላቸውምና
ወአውሥአ ወይቤሎሙ ሀብዎሙ አንትሙ ዘይበልዑ ።
እናንተም የሚበሉትን ስጧቸው አላቸው
ወይቤልዎ አርዳኢሁ ንሑር
ወንሣየጥ በ፪፻ ዲናር ኅብስተ
በሁለት ድሪም እንጀራ እንገዛ ዘንድ እንሂድን አሉት
፴፰ ወይቤሎሙ ሑሩ ወርእዩ ሚመጠን ኃባ ውዝ ብክሙ ።

፴፰ ምን ያህል እንጀራ እንዳለ ሄዳችሁ እዩ አላቸው ።
ወርእየሙ ይቤልዎ ኃምስ ኅብስት ወ፪ቲ ዓሣት
አይተው አምስት እንጀራ ሁለት ዓሣም አለ አሉት።

፴፱ ወአዘዞሙ ለኵሎሙ ያርፍቅዎሙ በበ ምርፋቃቲሆሙ ዲበ ሐመልማለ ሣዕር።ዮሐ ፮፡፲ ፡

፴፱ በለመለመ ሣር ላይ በየመቀመጫቸው ሁሉንም ያስቀምጧቸው ዘንድ አዘዛቸው ።

፵ ወረፈቁ በበምርፋቃቲሆሙ
፵ ተከፍለው ተከፍለው ተቀመጡ በበ፻ት መቶ መቶው
ወበበ፶ ።
አምሳ አምሳው አንድም መቶ መቶውን ባምሳ ሰደቃ አምሳ አምሳውን በመቶ ሰደቃ ።

፵፩ ወነሥኦን ለ፭ ኅብስት ወለክልኤቲ ዓሣት ወነጸረ ሰማየ ።
፵፩ አምስቱን እንጀራ ሁለቱንም ዓሣ ይዞ ወደሰማይ አየ ።
ወባረከ ።   ባረከም ።
ወፈተተ ኅብስተ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ያቅርቡ ሎሙ ። ኅብስቱን ቈርሶ ያቀርቡላቸው ዘንድ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው ።
ወከፈሎሙ ለኵሎሙ እም፪ቲ ዓሣትኒ ።
ሁለቱንም ዓሣ ለሁሉ ከፈለ
፵፪ ወበልዑ ኵሎሙ ወጸግቡ ።
፵፪ ሁሉም በልተው ጸገቡ ።
፵፫ ወአግኃሡ ዘተርፈ ፍትታተ ፲ ወ፪ተ መሳይምተ ።
፵፫ የተረፈውንም ቁራሽ ዐሥራ ሁለት መሶብ አነሱ ።
ወእምዓሣሁኒ ።
ዓሣውም ።
፵፬ ወእለሰ በልዕዎ ለውእቱ ኅብስት ዕደው ፶፻ት
፵፬ ያን እንጀራ የበሉት ሰዎች ግን ወንዶቹ አምስት ሽህ ናቸው ።

ዘከመ ሖረ ዲበ ማይ

፵፭ ወአዝበሮሙ ሶቤሃ ለአርዳኢሁ ይዕርጉ ሐመረ ወይቅድምዎ ማዕዶተ ቤተ ሳይዳ ፤
፵፭ ወደመርከብ ገብተው ወደቤተ ሳይዳ ወደ ማዶ ይቀድሙት ዘንድ በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ግድ አላቸው ።
እስከ ሶበ ይሥዕሮሙ ለሕዝብ ።
ሕዝቡን እስኪያሰናብት ድረስ ወእምድኅረ ፈነዎሙ ሖረ ወኃለፈ እምህየ ።
አሰናብቷቸው ከዚያ ወጣ ።
ወዓርገ ደብረ ከመ ይጸሊ ። ሊጸልይም ወደተራራ ወጣ ።

፵፯ ወመስዮ ብሔር ሀለወት ሐመር ማእከለ ባሕር ።

፵፯ በመሸም ጊዜ መርከቢቱ ከባሕር መካከል ነበረች ።
ወውእቱሰ ባሕቲቱ ሀሎ ውስተ ምድር ።
እሱ ግን ብቻውን በምድር ነበር ።

፵፰ ወርእዮሙ እንዘ የሐውሩ ወጥቀ ይትመነደቡ ።

፵፰ እጅግም እየተጨነቁ ሲሄዱ አያቸው ።
ወየሐምሞሙ ነፋስ ።
ነፋስም ያስጨንቃቸው ነበር
እስመ እምገጾሙ ውእቱ
ከወደፊታቸው ነውና ።

፵፰ ወበራብዕት ሰዓተ ሌሊት መጽአ ኀቤሆሙ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ የሐውር ዲበ ባሕር ማቴ ፲፬፡፳፭ ።

፵፰ ባራተኛው በዓተ ሌሊት ጌታ በባሕር ላይ እየሄደ መጣ ።
ወፈቀደ ይትዐደዎሙ
ሊያልፋቸውም ወደደ ፤

፵፱ ወሶበ ርእይዎ የሐውር ዲበ ባሕር መሰሎሙ ምትሐት ።

፵፱ በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ ምትሐት መሰላቸው ።

፶ ወኵሎሙ ርእይዎ ወደንገፁ
፶ ሁሉም አይተው ደነገጡ
ወአውየው ።
ጮሁም ።
ወነበቦሙ ሶቤሃ ።   ያን ጊዜ ተናገራቸው።
ወይቤሎሙ ተአመኑ ከመ አነ ውእቱ ።
እኔ እንደሆንኩ እመኑ አላቸው
ወኢትፍርሁ ፤
አትፍሩ ።

፶፩ ወዓርገ ኀቤሆሙ ውስተ ሐመር ።
፶፩ ወደመርከብ ወደላቸው ወጣ ።
ወሀደገ ነፋስ
ነፋስም ጸጥ አለ
ወፈድፋደ ተደሙ ፤
ፈጽመው ተደነቁ ።
ወአንከርዎ
አደነቁት ፤

፶፪ ወአመሂ ኅብስት ኢለበውዎ
፶፪ በእንጀራው ጊዜ አላስተዋሉም ነበር
እስመ ጽኑዕ ልቦሙ
ልቦናቸው ተሸፍኖባልና ።

ዘከመ ገብረ መንከራተ በጌንሴሬጥ
በገሚሠ ጽንፈ ልብስ ።

፶፫ ወሶበ አደዉ ወበጽሑ ምድረ ጌንሴሬጥ ማቴ ፲፬፡፴፬ ።

፶፫ ተሻግረውም ከጌንሴሬጥ ምድር በደረሱ ጊዜ አርሰዩ ሆየ ፤
ከዚያ መርከባቸውን አስጠጉ ።

፶፬ ወወፂኦሙ እምሐመር አእመርዎ ሶቤሃ ሰብአ ይእቲ ሀገር

፶፬ ከመርከቡም በወጡ ጊዜ ያን ጊዜ የዚያ አገር ሰዎች አወቁት ።

፶፭ ወሮጹ ውስተ ኵሉ በሐውርት ወአምጽኡ ድውያነ በአራታት

፶፭ ወደየሀገሩ ሮጡ ድውያንንም ባልጋ አመጡ
ወይወስዱ ኀበ ሰምዑ ከመ ሀሎ ውእቱ ሆየ
እሱ ያለበትን ወደሰሙበት ይወስዱቸዋል ።

፶፮ ወውስተ አኅጕር ወአዕጻዳት ኀበ ቦአ ውስተ ምሥያጣት ያነብርዎሙ ለድውያን ።

፶፮ ከገባበት ቦታና አገር ድውያንን ካደባባዩ ያኖሯቸው ነበር ወአስተብቍዕዎ ከመ ይግሥሦ ጽንፈ ልብሱ ።
የልብሱንም ጫፍ ይይዙ ዘንድ ማለዱት ፤
ወኵሎሙ እለ ገሠሥዎ የሐይዉ ።
የያዙትም ሁሉ ይድኑ ነበር ።

በእንተ ፈሪሳውያን ወሥርዓቶሙ

ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወተጋብኡ ኀቤሁ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መጺኦሙ እምኢየሩሳሌም ።

፩ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ከኢየሩሳሌም መጥተው ወደሱ ተሰበሰቡ ።

፪ ወርእይዎሙ ለአርዳኢሁ እንዘ ይበልዑ እክለ ዘእንበለ ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ። ማቴ ፲፭፡፪ ።

፪ ደቀ መዛሙርቱን እጃቸውን ሳይታጠቡ ሲበሉ አዩዋቸው ።

፫ እስመ ፈሪሳውያንሰ ወኵሎሙ አይሁድ ለእመ በሕቁ ኢተሐፅቡ እደዊሆሙ ኢይበልዑ እክለ

፫ ፈሪሳውያን ግን አይሁድ ሁሉ እጃቸውን በጅጉ ሳይታጠቡ አይበሉም ነበርና ። መላልሰውደም እስኪሰርበው እስኪመለጥ ድረስ ካልታጠቡ አይበሉም እስመ የዓቅቡ ሥርዓቶሙ ለረበናት ።
የረበናትን ሥርዓት ይጠብቁ ነበርና ።

፬ ወዘሂ ተሣየጡ እምሥያጥ ኢይበልዑ ለእመ ኢያጥመቅዎ ።

፬ ከገበያም የተገዛውንም በውኃ ካላጠቡ አይበሉ ፆምነበር ።
ወባዕደኒ ብዙኅ ኀርሙተ ዘይትዓቀቡ ።
ሌላም የሚጠብቁት ብዙ ሥርዓት አለ ።
ወያጠምቁ ጽዋዓተኒ
ጽዋውንም ያጥቡት ነበር ።
ወቈሳቍሳተ ።
ብርቱን ድስቱን ።
ወጽሕርታተ ፤
ማድጋውን ፤
ወአራታተ ፤ አልጋውን ።

፭ ወይቤልዎ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ለምንት ኢየሐውሩ አርዳኢከ በሕገ ሰርዐ ረበናት ።

፭ ጸሐፍት ፈሪሳውያንም ደቀ መዛሙርትህ እንደሽማግሌዎች ሥርዓት ለምን አይሄዱ አሉት ወዘእ ንበለ ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ይበልዑ እክለ ። እጃቸውንስ ሳይታጠቡ ለምን እህል ይበላሉ ።

፮ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ አመደልዎን ሠናየ ተነበየ ኢሳይያስ ላዕሌክሙ እንዘ ይብል ዝ ሕዝብ በከናፍሪሆሙ ያከብሩኒ ወልቦሙሰ ነዋኅ ይርኅቅ እምኔየ ። ኢሳ ፳፱ ፣ ፲፫ ።

፮ እናንት ግብዞች ኢሳይያስ።እኒህ ሕዝብ በከንፈራቸው ያከብሩኛል ልባቸው ግን ፈጽሞ ከኔ ይርቃሉ ብሎ ኢሳይያስ እውነት ተናግሮባችኋል ።
ወከንቶ ያመልኩኒ ።
በከንቱ ያመልኩኛል ።

፯ እንዘ ይሜህሩ ሥርዓታተ ትእዛዛተ ሰብእ።
፯ በሰዎች ሥርዓት ትምህርት እያስተማሩ ።
፰ ወየኃድጉ ትእዛዛተ እግዚአብሔር ወየዓቅቡ ትእዛዘ እጓለ እመሕያው ።

፰ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትተው የሰውን ሥርዓት ይጠብቁ ነበረና ። ዋምቀታተ
ጽዋዓት ወቍሳቍሳተ
ጽዋውን ብርቱን ድስቱንም ማጠብ ።
ወጽርሕታተ ።
ማድጋውን ወባዕደኒ ብዙኀ ዘይመስሎ ለዝንቱ ።
ሌላውንም ይህን የመሰለውን ሁሉ ።
፱ ወይቤሎሙ ርቱዕኑ ትዕልው ትእዛዛተ እግዚአብሔር ከመ ትዕቀቡ ትእዛዘ ርእስክሙ ፤
፱ የራሳችሁን ትእዛዝ ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ልታፈርሱ ይገባልን አላቸው ።
፲ ወሙሴ ይቤለክሙ አክብር አባከ ወእመከ ዘፀ ፳ ፣ ፲፪ ። ዘዳ ፭ ፣ ፲፮ ። ኤፌ ፮ ፣ ፪ ። ዘፀ ፳፩ ፣ ፲፯ ። ዘሌ ፳ ፣ ፱ ። ምሳ ፳ ፣ ፳ ።
፲ ሙሴ እናትትና አባትትክን አክብር ብሏችኋል ወዘአኅሠመ ቃለ ላዕለ አቡሁ ወእሙ ሞተ ለይሙት አባትና እናቱንም የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ።

፲፩ ወአንትሙሰ ትብልዎ ዘይቤሎ ለአቡሁ
፲፩ እናንተ ግን ላባቱ የሚመልሰውን ትነግ ሩታላችሁ ፤
አው ለእሙ ፤
ወይም ለናቱ የሚመልሰውን ቊርባን ዘረባህከ እምኔየ ብሂል ከኔ ያገኘኸውን ቊርባን ነው ማለት ነው፤

፲፪ ኢታበውህዎ ይግበር ምንተኒ ለአቡሁ ወለእሙ ።

፲፪ ላባትና ለናቱ ምን ምን ያደርግ ዘንድ አታሰናብቱትም ፤

፲፫ ወትሥዕሩ ቃለ እግዚአብሔር በእንተ ትእዛዝ ዘሠራዕክሙ ።

፲፫ ለሠራችሁት ሥራት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ታፈርሳላችሁ ።
ወዓዲ ብዙኀ በአምሳለ ዝንቱ ዘትገብሩ ።
ዳግመኛም ሌላም የምትሠሩት ይህን የመሠለ ብዙ አለ
፲፬ ወጸውዖሙ ካዕበ ለሕዝብ ወይቤሎሙ ስምዑ ኵልክሙ ወለብው ። ማቴ ፲፭ ፣ ፲ ።
፲፬ ሁለተኛ ሕዝቡን ጠርቶ ስሙ እወቁ አላቸው
፲፭ አልቦ ዘይበውእ እምአፍአ ውስተ አፉሁ ለሰብእ ዘይክል አርኵሶቶ ።
፲፭ ከውጭ ወደ ሰው አፍ የሚገባው ሊያረክሰው አይችልም ዘእንበለ ዳዕሙ ዘይወፅእ እምልቡ ለሰብእ ውእቱ ያረኵሶ ለሰብእ ።
ከሰው ልብ የሚወጣ እሱ ያረክሰዋል እንጂ ፤
፲፮ ዘቦ እዝን ሰሚዓ ለይስማዕ ፤
፲፮ ጆሮ ያለው ይስማ ።
ወበዊአ ቤተ እምኀበ ሕዝብ ተስእልዎ አርዳኢሁ ዘንተ አምሳለ ።
ከሕዝቡም ዘንድ ወደ ቤት በገባ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ይህን ምሳሌ ጠየቁት ፤
፲፯ ወይቤሎሙ እንትሙኒ ከመዝኑ ኢትሌብዉ
፲፯ እናንተም እንዲህ ገና አታውቁምን
፲፰ ኢተአምሩኑ ከመ ኵሉ ዘእምአፍኣ ይበውእ ውስተ ሰብእ ኢይክል አርኵሶቶ ።
፲፰ ከውጭ ወደ ሰው የሚገባው ሁሉ ሰውን እንዳይጐዳው አታውቁምን ።
፲፱ እስመ ኢይበውእ ውስተ ልቡ ዘእንበለ ውስተ ከርሡ ከመ ።
፲፱ ወደ ሆዱ ብቻ ነው እንጂ ወደ ልቡ አይገባምና ።
ወጽመ ይትከዓው እንዘ ያነጽሕ ኵሎ መባልዕተ
መብሉን ሁሉ ሲያጠራ ቆይቶም ይወጣል ።
፳ ወይቤሎሙ ዘይወጽእ እምአፉሁ ለሰብእ ውእቱ ያረኵሶ ለሰብእ ።
፳ ከሰው የሚወጣው እሱም ሰውን ይጐዳዋል ዘፍ ፮ ፣ ፭ ።

፳፩ እስመ እምውሥጠ ልቡ ለሰብእ ይወጽእ ኵሉ ሕሊና እኩይ

፳፩ ከሰው ከልቡ ውሥጥ ክፉ አሳብ ሁሉ ይወጣልና ።
ዘውእቱ ዝሙት ፤
ይህም ዝሙት ነው

ወቀቲል	መግደል ።
ወሰርቅ	
መስረቅ	

፳፪ ወሐዊረ ብእሲተ ብእሲ
፳፪ ወደ ጕልማሳ ሚስት መሄድ

ወትዕግልት	ቅሚያ
ወእከይ	ክፋት ።
ወጕሕሉት	ክዳት
ወጽልሑት	ሽንገላ ።
ወምርዓት	ድርዓት
ወጽርፈት	ስድብ ።
ወትዕቢት	ትዕቢት
ወሕሙሚ ዓይን	ምቀኝነት
ወዕበድ	ስንፍና ።

፳፫ ዝንቱ ኵሉ እኩይ ይወጽእ
፳፫ እምውሥጥ ይህ ሁሉ ክፉ
ነገር ከውስጥ ይወጣል
ወያረኵሶ ለሰብእ ።
ሰውን ይጐዳዋል ፤

በእንተ ከነናዊት ።

፳፬ ወተንሥአ እግዚእ ኢየሱስ እምህየ ሖረ ብሔረ ጢሮስ ወሲዶና ፤ ማቴ ፲፭፥፳፩ ።

፳፬ ጌታም ከዚያ ተነሥቶ ወደጢሮስና ወደ ሲዶና ሄደ ።
ወቦአ ቤተ ወኢፈቀደ ያእምሮ መኑሂ ።
ከቤትም ገባ ማንም ማን ሊያውቀው አልወደደም።
ወስእነ ተከብቶ ።
መሠወርም አልተቻለውም
፳፭ ወእምዝ ሰምዓት በእንቲአሁ አሐቲ ብእሲት እንተ ጋኔን እኩይ አኀዛ ለወለታ ፤
፳፭ ከዚህም በኋላ ልጅዋን ርኩስ ጋኔን የያዘባት አንዲት ሴት የሱን ነገር ሰማች ።
ወቦአት ወሰገደት ሎቱ ታሕተ እገሪሁ ።
ገብታም ከእግሩ በታች ሰገደችለት ።
፳፮ ወአረማዊት ይእቲ ብእሲት ፤
፳፮ ያችም ሴት አረማዊት ናት ።
ወሲሮፊኒቂሳዊት ።
ሲሮፊኒቂሳዊትም ናት ሐተታ አረማዊት ከነናዊት ከነዓናዊት ጽርአዊት ሶርያዊት ሲሮፊንቂሳዊት ይላታል ስምንት ጋዋ ያላት ናት የሰው ትውልድ ከብዙ ወገን ነውና ።
ወሰአለቶ ያውጽእ ጋኔነ እምወለታ ።
ከልጅዋ ጋኔን ያወጣላት ዘንድ ለመነችው

፳፯ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ኅድጊ ቅድመ ምዕረ ይጽገቡ ውሉድ ፤

፳፯ ጌታም ቀድሞ ልጆች ይጽገቡ አላት ።
እስመ አኮ ሠናይ ነሚእ ኅብስተ ውሉድ ወውሂቦ ለከለባት ።
የልጆችን እንጀራ ነሥቶ ለውሾች መስጠት አይገባምና ፤

፳፰ ወተሰጥወቶ ።
መለሰችለት ።
ወትቤሎ እወ እግዚኦ ከለባትኒ ይበልዑ በታሕተ ማዕድ ፍርፋሬ ዘያወድቁ ደቂቅ ።

፳፰ አዎን አቤቱ ውሾች ልጆች ከማዕድ የጣሉትን ፍርፋሪ ይበላሉ አለችው ።
፳፱ ወይቤላ በዝንቱ ቃልኪ ሑሪ ወጽአ ውእቱ ጋኔን እምወለትኪ
፳፱ ስለዚህም ነገርሽ ሂጂ ጋኔኑም ከልጅሽ ወጥቷል አላት ።
፴ ወሖረት ወአተወት ቤታ
፴ ወደቤቷም ተመለሰች ።
ወረከበታ ለወለታ ልብስታ ወትነብር ዲበ ዓራታ
ልጅዋን ልብሷንም ለብሳ ባልጋውም ተቀምጣ አገኘቻት ወኃደጋ ጋኔና ።
ጋኔኑዋም ተዋት ።

ዘከመ ፈወሶ ለበሐም ወጽሙም ።

፴፩ ወኃሊፎ ካዕበ እምጢሮስ ወሖረ እንተ ሲዶና ወባሕረ ገሊላ እንተ ፲ቱ አኅጉር ።
፴፩ ዳግመኛ ከጢሮስ አልፎ ባሥሩ ሀገር መካከል ወደ ገሊላ ባሕርዋ ወደ ሲዶና ሄደ ።
፴፪ ወአምጽኡ ኀቤሁ በሐመ ወጽሙመ ።
ማቴ ፱፥፴፪ ሉቃ ፲፩፥፲፬ ።
፴፪ ደንቆሮም ድዳም ይዘው ወደሱ መጡ ።
ወአስተበቍዕዎ ከመ ይደይ እዴሁ ላዕሌሁ ።
እጁንም ይጭንበት ዘንድ ማለዱት ።
፴፫ ወአግኃሦ እምሰብእ ባሕቲቱ
፴፫ ብቻውንም ከሰው ለየው
ወወደየ አፃብዒሁ ውስተ እዘኒሁ
ጣቱንም ከጆሮው ጫነበት
ወተፍአ ፤
ምራቁንም ተፋበት ፤
ወገሠሠ ልሳኖ ፤
ምላሱንም ዳሰሰው ።
፴፬ ወነጸረ ሰማየ ፤
፴፬ ወደሰማይ አየ ፤
ወአስተምሐረ ።
አዘነም ፤

ወይቤ ኤፍታሔ ኤፍታሔ
ኤፍታሔ ኤፍታሔ አለ
ተረጎው ብሂል
ተከፈት ማለት ነው ።
፴፭ ወሶቤሃ ተከሥተ ዕዘኒሁ ።
፴፭ ያንጊዜም ጆሮው ተከፈተ ።
ወተፈትሐ ማዕሠረ ልሳኑ
የምላሱም ዕሥራት ተፈታ
ወተናገረ ርቱዓ
አቃንቶም ተናገረ
፴፮ ወገሠፆሙ ኢይንግሩ ወኢለ
፴፮ መኑሂ ለማንም
ለማን እንዳይናገሩ ገሠፃቸው ።
ወአምጣነ ይከልዖሙ ውእቱ ፈድፋደ ይነግሩ ሎቱ
እሳቸው ግን በከለከላቸው መጠን ይናገሩ ነበር ።
፴፯ ወፈድፋደ ያነክርዎ ወእንዘ ይብሉ ሚሠናይ ኵሉ ዘገብረ ዝንቱ ብእሲ ።

፴፯ ይህ ሰው የሠራው ምን ያማር እያሉ ፈጽመው ያደንቃሉ ለጽሙማን ያሰምዖሙ
ደንቆሮዎችን ያሰማቸዋል
ወለበሐማን ያነብቦሙ
ዲዳዎችን ያናግራቸዋል ።

በከመ አብዝኀ ኅብስተ ዳግመ ።

ምዕራፍ ፰ ።

፩ ወይእተ አሚረ ካዕበ ብዙኅ ሰብእ እንዘ ሀሎ አልቦሙ ዘይበልዑ ማቴ ፲፭፥፴፪ ።

፩ በዚያም ወራት ብዙ ሰው ሳለ የሚበሉት አልነበራቸውም ።

፪ ወጸውዖሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ያምሕሩኒ እሉ ሰብእ
፪ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ እኒህ ሰዎች ያሳዝኑኛል አላቸው ።
ናሁ ሣልሶሙ ዮም እንዘ ይጸንሑኒ ።
፫ ሲጠብቁኝ ሦስተኛ ቀናቸው ነውና ።
ወአልቦሙ ዘይበልዑ
የሚበሉትም የላቸውም
፫ ወእመኒ ሠዓርክዎሙ ርኁባኒሆሙ ይእትዉ አብያቲሆሙ ይደክሙ በፍኖት ።

፫ ወደ ቤታቸውም ይገቡ ዘንድ ተርበውም ባሰናብታቸው በመንገድ ይደክማሉ ።
ወእለሂ መጽኡ እምርኁቅ
ከሩቅም የመጡ አሉ ።
፬ ወይቤልዎ አርዳኢሁ መኑ ዘይክል በዝየ በገዳም አጽግቦቶሙ ኅብስተ ለዝንቱ ኵሉ ሕዝብ
፬ ደቀ መዛሙርቱ በዚህ በገዳም ይህን ሁሉ ሕዝብ ማጽገብ የሚቻለው ማነው አሉ ፡

፭ ወይቤሎሙ ሚመጠን ኅብስትክሙ ።
፭ ምን ያህል እንጀራ አላችሁ አላቸው
ወይቤልዎ ሰብኡ
ሰባት ነው አሉት ።

፮ ወአዘዞሙ ለሰብእ ይርፍቁ ዲበ ምድር
፮ ሰዎቹን ከምድር ይቀመጡ ዘንድ አዘዛቸው
ወነሥአን ለሰብኡ ኅብስት
ሰባቱንም እንጀራ ያዘ ።
ወአዕኰተ አመሰገነ
ወፈተተ። ቈረሰ
ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ያቅርቡ ሎሙ ለሕዝብ
ያቀርቡላቸው ዘንድ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው ።
ወአቅረቡ ለሰብእ
ለሰዎችም አቀረቡ

፯ ወቦሙ ዓሣነ ኅዳጠ
፯ ጥቂት ዓሣም ነበራቸው ።
ወባረከ ኪያሆኒ
ያንም ባረከው ።
ወይቤሎሙ አቅርቡ ሎሙ ዘኒ
ይህን አቅርቡላቸው አላቸው ።

፰ ወበልዑ ወጸግቡ ።
፰ በልተውም ጠገቡ
ወዘአግኃሡ ዘተርፈ ፍተታተ መልዓ ፯ተ አስፈሬዳተ ።
ያነሡት የቍራሽ ትራፊ ሰባት እንቅብ መላ ።

፱ ወእለሰ በልዑ የአክሉ ፵፻ ።
፱ የበሉትም አራት ሺህ ያህላሉ ወእምዝ ፈነዎሙ ሶቤሃ ይሑሩ ።
ከዚህም በኋላ ይሄዱ ዘንድ አሰናበታቸው ።

፲ ወእምዝ ዓርገ ሐመረ ምስለ አርዳኢሁ ወበጽሐ ውስተ ደወለ ድልማኑታ ።

፲ ከዚህም በኋላ ከመርከብ ገብቶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ወደ ድልማኑታ ሄደ ።

ዘከመ ኀሠሡ ትእምርተ እምሰማይ ።

፲፩ ወወጽኡ ፈሪሳውያን ። ማቴ ፲፥ ፮፥ ፩ ሉቃ ፲፩፥ ፲፮ ።
፲፩ ፈሪሳውያንም ወጡ ።
አኀዙ ይትኀሠሥዎ
ይከራከሩትም ጀመር
ወሰአልዎ ትእምርተ እምሰማይ እንዘ ያሜክርዎ
ሲፈትኑት ከሰማይ ምልክት ለመኑት ።
፲፪ ወተከዘ በመንፈሱ
፲፪ በልቡም ተቈረቈረ
ወይቤ ምንትኑ ተኃሥሥ ትእምርተ ዛቲ ትውልድ
ይች ትውልድ ለምን ምልክት ትሻለች ።
፲፫ አማን እብለክሙ ከመ ኢይትወሀባ ለዛቲ ትውልድ ትእምርት ።

፲፪ ለዚህች ትውልድ ምልክት አይሰጣትም
ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።
ወኃደጎሙ ወዓርገ ካዕበ ሐመረ ወሖረ ማዕዶተ።
ትቷቸው ሁለተኛ በመርከብ ተጭኖ ወደ ማዶ ሄደ።

፲፬ ወረስዑ ነሢአ ኅብስተ ማቴ ፲፮ ፡ ፭ ፡
፲፬ እንጀራ መውሰድን ረሱ
ወአልቦሙ ዘእንበለ አሐቲ ኅብስት ምስሌሆሙ
ውስተ ሐመር
እርሳቸውም ካንዲት እንጀራ በቀር በመርከብ አል
ነበራቸውም ሐተታ ማቴዎስ ዘእንበለ አሐቲ አሳ
ለም ማርቆስ ዘእንበለ አሐቲ አለ እንደምን ነው
አይጣላም ቢሉ አይጣላም ካነስ ዘንድ የለም ማለት
ልማድ ነውና ማቴዎስ ዘእንበለ አሐቲ አላለም
ወበውስተ ውሁድኒ ንብል አልቦ እንዲል እንድም
ማርቆስ አንዲት ሳትቀር ሲል ነው ። አግብኡ ሊተ
ንዋይየ ዘእንበለ ብእሲትየ እንዲል ።

፲፭ አዘዞሙ ወይቤሎሙ ዑቁ ወተዓቀቡ እምነ
ብሑዓ ፈሪሳውያን ወእምነ ብሑእሙ ለሄሮድሳ
ውያን ።

፲፭ ከሄሮድሳውያንና ከፈሪሳውያን እርሾ አስ
ተውላችሁ ተጠበቁ ብሎ አዘዛቸው ።

፲፮ ወሐለዩ በበይናቲሆሙ
፲፮ እስበባቸው እስመ ወይቤሉ
እስመሁ ኅብስተ ኢነሥአነ ።
እንጀራ ስለአልያዝን ነውን አሉ

፲፯ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ
ምንተ ትሔልዩ በልብክሙ ።

፲፯ ጌታም አውቆባቸው በልባችሁ ምን ታስ
ባላችሁ አላቸው ።
እስመሁ ኅብስት አልብክሙ
እንጀራ የሳችሁምና ነው ።
ዓዲኑ ተአምሩ ወኢትሌብዉ ገና አላወቃችሁም
ልብ አላረጋችሁም ።
ልብክሙኑ ጽሉል
ልባችሁ ደንቆሮ ነውን
፲፰ ወአዕይንት ብክሙ ወኢትሬእዩ ማር ፬
፲፪ ዮሐ ፲ ፲፩
፲፰ ዓይን አላችሁ አታዩም
ወዕዝን ብክሙ ወኢትሰምዑ ጆሮም አላችሁ አት
ሰሙም ወኢትዜከሩኑ ።
አታስቡምን
፲፱ ዘአመ ኃምሰ ኅብስት ፈተትኩ ለ፶፻ ብእሲ
፲፱ ላምስት ሺህ ሰው አምስት እንጀራ
በቈረስኩ ጊዜ ።
ሚመጠነ አግኃሥክሙ አክፋረ ዘመልዓ ፍተታተ
ዘተርፈ፡የተረፈውን ቁራሽ ምን ያህል ቅርጫት የመላ
አነሳችሁ አላቸው ።

ወይቤልዎ ፲ተ ወ፪ተ
አሥራ ሁለት ነው አሉት

፳ ወይቤሎሙ አመኒ ሰብዐ ኅብስተ ለ፬፻
ብእሲ ሚመጠነ አግኃሥክሙ አስፈሬዳተ ዘመልዓ
ፍተታተ ዘተርፈ ።

፳ ላራት ሺህ ሰው ሰባት እንጀራ በቈረስኩ
ጊዜ የተረፈውን ቁራሽ ስንት እንቅብ የመላ አነሳችሁ
ወይቤልዎ ሰብዐ
ሰባት ነው አሉት ።

፳፩ ወይቤሎሙ እፎ እንከ ዘኢትሌብዉ
፳፩ እንኪያ አለማስተዋላችሁ እንደምን ነው
አላቸው ።

በእንተ ዕዉር ዘቤተ ሳይዳ ።

፳፪ ወበጺሖሙ ቤተ ሳይዳ አምጽኡ ኀቤሁ
ዕውረ ።

፳፪ ወደ ቤተ ሳይዳም በደረሱ ጊዜ ዕውርን
ወደሱ አመጡ
ወአስተብቍዕዎ ይግሥሦ
ይዳስሰው ዘንድ ማለዱት
፳፫ ወአኀዞ በእዴሁ ለውእቱ ዕውር ወአው
ፅኦ አፍአ እምሀገር
፳፫ ያን ዕውር በጁ ይዞ ከሀገርም አፍአ
አወጣው ።
ወተፍዓ ውስተ አዕይንቲሁ
ባይኑም ተፋበት
ወገሠሦ ዳሰሰውም
ወይቤሎ ምንተ ትሬኢ
ምን ታያለህ አለው
፳፬ ወነጸረ ወይቤ እሬኢ ሰብአ ከመ ዕፀው
ያንሶስዉ
፳፬ እይቶ ሰዎች እንደዛፍ ሲመላለሱ አያለሁ
አለ ። ሐተታ ዕውር ሆኖ ተወልዷል ያሉ እንደሆነ
በምን ዐወቀ ቢሉ ፀበትሩ ከተወለደ በኋላ ታውሯል
ያሉ እንደሆነ የተመቸ ።
፳፭ ወገሠሦ አዕይንቲሁ ካዕበ
፳፭ ሁለተኛ አይኑን ዳሰሰው
ወርእየ ዳኅነ
ፍጹም ብርሃን አየ
ወነጸረ ኵሎ ብሩሃ
ሁሉን ገልጦ አየ ።
፳፮ ወፈነዎ ቤቶ
፳፮ ወደ ቤቱም ሰደደው
ወይቤሎ ኢትባእ ውስተ አዕፃዳት
ወደ መንደርም አትግባ ።
ወአልቦ ዘትነግር በውስተ ሀገርኒ
በመንደርም ለማንም አትናገር አለው።ሐተታ ዕውር
የባሕታውያን ምሳሌ ጥቂት ጸጋ የተሰጣቸው እንደ

ሆነ ሰውን ሁሉ በግዕዝ እንስሳ ያዩታል ሁለተኛ ቢዳስሰው ፈጽሞ አንዳየ ፍጹም ጸጋ የተሰጣቸው እንደሆነ ኃጥእ ጻድቅ አማኒ መናፍቅ ሳይለዩ ሁሉን ይወዳሉና ።

በእንተ ተአምኖተ ጴጥሮስ ።

፳፯ ወሖረ እግዚእ ኢየሱስ ወአርዳኢሁ፡ውስተ አኅጉረ ቂሣርያ ዘፊልጶስ ማቴ ፲፮፡፲፫ ሉቃ ፱፡፲፰

፳፯ ጌታ ወደ ፊልጶስ አገር ወደ ቂሣርያ መንደሮች ሄደ ።
ወተስእሎሙ ለአርዳኢሁ በፍኖት መኑ ይብለኒ ሰብእ ከመ አነ ውእቱ ።
እኔ እንደሆንኩ ሰው ማን ይለኛል ብሎ ደቀ መዛሙርቱን በመንገድ ጠየቃቸው ።
፳፰ ወይቤልዎ ዮሐንስሃ መጥምቀ ፤
፳፰ ዮሐንስ መጥምቅን ይሉሃል ።
አው ኤልያስሃ ።
ወይም ኤልያስን
አው ፩ዱ እምነቢያት
ወይም ከነቢያት አንዱን ይሉሃል አሉት ፤
፳፱ ወይቤሎሙ አንትሙኬ መኑ ትብሉኒ
፳፱ እናንተስ ማነው ትሉኛላችሁ አላቸው
ወተሠጥዎ ጴጥሮስ ወይቤሎ አንተ ውእቱ ክርስቶስ
ጴጥሮስም አንተ ክርስቶስ ነህ ብሎ መለሰ ።
፴ ወገሠፆሙ ከመ ኢይንግሩ ወኢለመኑሂ በእንቲአሁ ።

፴ ለማንም ሰማን እንዳይናገሩ ገሠፃቸው ።

በእንተ ትንቢት ዘሕማማት

፴፩ ወአኀዘ ይምሐሮሙ ከመ ሐለዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው ብዙኀ ያሕምምዎ ወያመክርዎ ረበናት ወሊቃነ ካህናት ።
፴፩ ጌታም ሽማግሎች የካህናት አለቆች ይፈትኑት ዘንድና ብዙ መከራ ያመጡትበት ዘንድ እንዳለው ያስተምራቸው ጀመር ፤
ወይቀትልዎ ።
እንዲገድሉት ።
ወይትነሣእ በሣልስት ዕለት ።
በሦስተኛውም ቀን እንዲነሳ ፤
፴፪ ወገሃደ ነገሮሙ ዘንተ ነገረ ።
፴፪ ይህንም ነገር ገልጦ ነገራቸው ።
ወአኀዘ ይገሥፆ ።
ይቆጣውም ጀመር ።
፴፫ ወተመይጠ ወነጸረ ኀበ አርዳኢሁ ።
፴፫ ተመልሶም ወደ ደቀ መዛሙርቱ አየ ።
ወገሠፆ ለጴጥሮስ ።
ጴጥሮስንም ተቆጣው ።
ወይቤሎ ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን ።
አንተ ሰይጣን ከኋላዬም ሂድ አለው ።
እስመ ኢትሄሊ ዘእግዚአብሔር ዘእንበለ ዘእጓለ እመሕያው ።
የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ።

በእንተ ኀዲገ ርእስ ዘክርስቲያን ።

፴፬ ወጸውዖሙ ለሕዝብ ምስለ አርዳኢሁ ። ማቴ ፲ ፡ ፴፰ ፤ ፲፮ ፡ ፳፬ ሉቃ ፱ ፡ ፳፫ ፤ ፲፬ ፡ ፳፯
፴፬ ሕዝቡን ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ጠራቸው ።
ወይቤሎሙ ዘይፈቅድ ይጸመደኒ ይጽልዕ ለነፍሱ ወያጥብዕ ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ ወይትልወኒ ።
ሊያገለግለኝም የሚወድ ጨክኖ የሞትን መስቀል ተሸክሞ ይከተለኝ አላቸው ።
፴፭ ዘይፈቅድ ያድኅና ለነፍሱ ለይግድፋ ሉቃ ፲፯ ፡ ፴፫ ዮሐ ፲፪ ፡ ፳፭ ።
፴፭ ነፍሱን ሊያድናት የወደደ ይጣላት ።
ወዘገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ ወበእንተ ወንጌል ይረክባ
ስለኔ ስለ ወንጌልም ነፍሱን የጣለ ያገኛታል ማለት ያድናታል ።
፴፮ ወምንት ይበቍዖ ለሰብእ ለእመ ኮሎ ዓለመ ረብሐ ወነፍሶ ኀጕለ ።
፴፮ ነፍሱን ካጣ ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ለሰው ምን ይረባዋል ።
፴፯ ወምንት እምወሀበ ሰብእ ቤዛሃ ለነፍሱ ።
፴፯ ወይስ ለነፍሱ ቤዛ ሰው ምን በሰጠ ።
፴፰ ወዘኒ ኀፈረኒ ወኀፈረ ቃልየ በዛቲ ትውልድ ዘማ ወኃጥእት ። ማቴ ፲ ፡ ፴፫ ። ሉቃ ፱ ፡ ፳፮ ፡ ፲፪ ፡ ፱ ።
፴፰ ዘማ ኃጢአተኛም በምትሆን በዚህች ትውልድ ያፈረኝን በነገሬም ያፈረውን ፤
ወልደ እጓለ እመሕያውኒ የኀፍሮ አመ ይመጽእ ።
በስብሐተ አቡሁ ምስለ መላእክቲሁ ቅዱሳን
ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስም ባባቱ ምስጋና ከቅዱሳን መላእክት ጋራ በመጣ ጊዜ ያፍረዋል ።

ምዕራፍ ፱ ።

፩ ወይቤሎሙ ሀለው እምእለ ይቀውሙ ዝየ እለ ኢይጥዕምዎ ለሞት እስከ ይሬእይዋ ለመንግሥተ እግዚአብሔር እንዘ ትመጽእ በኃይል ማቴ ፲፮ ፡ ፳፰ ። ሉቃ ፱ ፡ ፳፯ ።

፩ የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል መጥታ እስኪያዩዋት ድረስ ከዚህ ቁመው ካሉት ሞትን የማይቀምሷት አሉ ብዬ እነግራችኋለሁ ።

ዘከመ ተወለጠ ራዕዩ በደብረ ታቦር ።

፪ ወእመ ሰዱስ ዕለት ነሥኦሙ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ ።

፪ ኢየሱስ በስድስተኛው ቀን ጴጥሮስን ያዕቆብንና ዮሐንስንም ወሰዳቸው ።

ወዓሪጎሙ ደብረ ነዋኀ በባሕቲቶሙ ።
ለብቻቸውም ወደ ረጅም ተራራ አወጣቸው ።
ወተወለጠ ራእዩ በቅድሜሆሙ ።
መልኩም በፊታቸው ተለወጠ ።

፫ ወአልባሲሁኒ በረቀ ወፃዕደወ ጥቀ ።
፫ ልብሱ አበራ እጅግም ነጭ ሆነ ።
ወኢይክል መሐፒል ከማሁ አፃዕድዎቶ በዲበ ምድር
በምድር ላይ ሸማ አጣቢ እንደሱ ነጭ ማድረግ የማይቻለው አንድም መሐፒል ሳሙና ነው ።

፬ ወአስተርአይዎሙ ሙሴ ወኤልያስ እንዘ ይትናገሩ ምስለ እግዚእ ኢየሱስ ።

፬ ኤልያስና ሙሴ ከጌታ ጋራ ሲነጋገሩ ታዩዋቸው ።

፭ ወአውሥአ ጴጥሮስ ።
፭ ጴጥሮስ መለሰ ።
ወይቤሎ ለእግዚእ ኢየሱስ ረቢ ይኄይሰነ ንንበር ዝየ
መምህር ከዚህ ብንቀመጥ ለኛ መልካም ነው ።
ወንግበር ሠለስተ ማኅደረ ።
ሦስትም ዳስ እንሥራ አለው ።
፩ደ ለከ ። አንዱን ላንተ ። ወ፩ደ ለሙሴ ። ወ፩ደ ለኤልያስ ።
አንዱንም ለሙሴ ። አንዱንም ለኤልያስ ።
ወኢየአምር ዘይብል ።
የሚናገረውን አያውቅም ነበር ።
እስመ ድንጉፃን እሙንቱ ።
ደንግጠውም ነበርና ።
፮ ወመጽአ ደመና ብሩህ ወጸለሎሙ ።
፮ ብሩህ ደመና መጥቶም ሠወራቸው ።
ወመጽአ ቃል እምደመና ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ።
ከደመናም የምወደው ልጄ ይህ ነው ።
ወሎቱ ስምዕዎ ።
የሱንም ስሙት የሚል ቃል ተሰማ ።
፯ ወእምዝ ነጸሮሙ ግብተ አልቦ ዘርእዩ ዘእንበለ እግዚእ ኢየሱስ ባሕቲቱ ምስሌሆሙ ።
፯ ድንገትም በተመለከቱ ጊዜ ጌታን ብቻ ከሳቸው ጋራ ነው እንጂ ያዩት የለም ።
፰ ወእንዘ ይወርዱ እምደብር አዘዞሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢይንግሩ ወኢለመኑሂ ዘርእዩ ዘእንበለ አመ ተንሥአ ወልደ እጓለ እመሕያው እምነ ምውታን ማቴ ፲፯ ፥ ፱ ።
፰ ከተራራም ሲወርዱ ጌታ የሰው ልጅ ከሙታን በተነሣ ጊዜ ነው እንጂ ሳይነሣ ያዩትን ለማንም ለማን እንዳይናገሩ አዘዛቸው ።
፱ ወዓቀቡ ቃሎ ። ሚል ፱ ፥ ፭ ።
፱ ነገሩንም አስተዋሉ ።
ወኃሠሥዎ ምንት ውእቱ ተንሥኦ እምነ ምውታን ።
ከሙታን መነሣት ምንም እንደሆነ ተመራመሩ ።

፲ ወተስአልዎ አርዳኢሁ ወይቤልዎ ይቤሉ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ኤልያስ ይቀድም መጺአ ።
ኢሳ ፶፫ ፥ ፫ ፤ ፱ ፥ ፭ ።

፲ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ኤልያስ አስቀድሞ ይመጣል ይላሉ ብለው ጠየቁት ።

፲፩ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ኤልያስ ይመጽእ ቅድመ ወያስተራትዕ ኵሎ ።

፲፩ ኤልያስ አስቀድሞ መጥቶ ሁሉን ያቅናናል ብሎ መለሰላቸው ።
ወአፎ ጽሑፍ በእንተ ወልደ እጓለ እመሕያው ከመ ብዙኀ የሐምምዎ ወይሜንንዎ ።
በሰው ልጅ መከራ እንዲያመጡበት እንዲንቁትም እንደምንስ ተጻፈ ።

፲፪ ወባሕቱ እብለክሙ ኤልያስ ወድአ መጽአ ማቴ ፲፯ ፥ ፲፪ ።
፲፪ ነገር ግን ኤልያስ ፈጽሞ እንደመጣ ።
ወገብሩ ላዕሌሁ ኵሎ ዘፈቀዱ በከመ ጽሑፍ በእንቲአሁ ።
ስለሱ እንደ ተጻፈ የወደዱትንም ሁሉ እንዳደረጉበት እነግራችኋለሁ ።
፲፫ ወመጽአ ኀበ አርዳኢሁ ።
፲፫ ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ ወረከበ ብዙኃነ ሰብአ ኀቤሆሙ ።
ከሳቸውም ዘንድ ብዙ ሰው አገኘ ።
ወጸሐፍትኒ እንዘ ይትኃሥልዎሙ ጸሐፍቶችም ሲጠይቋቸው ።
በእንተ ዘከመ ሐይወ ዘአስተራኀየ ጋኔኑ ።
፲፬ ወሶበ ርእይዎሙ ኵሎሙ ሰብአ ደንገጹ ወሮጹ ሶቤሃ ወአምኃዎ ።
፲፬ ሰዎችም ባዩት ጊዜ ደንግጠው ያንጊዜውንም ሮጠው ተገናኙት ።
፲፭ ወተስአሎሙ ለጸሐፍት ።
፲፭ ጸሐፍትን ጠየቃቸው ።
ምንተኑ ትትኃሠሥዎሙ ።
ለምን ትመራመሯቸዋላችሁ ።
፲፮ ወአውሥአ ፩ዱ እምውስተ አሕዛብ ። ሉቃ ፱ ፥ ፴፰ ።
፲፮ ከአሕዛብ አንዱ መለሰ ።
ወይቤሎ ሊቅ አምጻእክዎ ለወልድየ ኀቤከ ።
መምህር ሆይ ልጄን ወደ አንተ አምጥቼዋለሁ ።
እስመ ጋኔን በሐም አኀዞ ።
ድዳ ጋኔን አድሮበታልና ።
፲፯ ወሀበ ረከቦ ይነጽሖ ።
፲፯ ባገኘውም ሥፍራ ሁሉ ይጥለዋል ።

ወያስተራግፆ ።	ያራግጠዋልም ።
ወያሴውኖ ።	ያስለግገዋልም ።
ወያስይኖ ።	ያሸነዋል ።
ያስንኖ ።	ስምንምን ያደርገዋል ።

ወየሐቅዮ ስነኒሁ ። ጥርሱንም ያፋጫል ።
ያየብስ ። ያደርቀውማል ።
ወእቤሎሙ ለአርዳኢከ ያውፅእዎ ።
ደቀ መዛሙርትህንም ያወጡት ዘንድ አልኳቸው ።
ወስዕንዎ ፈውሶቶ ። መፈወሱም ተሳናቸው

፲፰ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ኦ ትውልድ እንተ አልባቲ ሃይማኖት እስከ ማዕዜኑ እሄሉ ምስሌክሙ ።

፲፰ እናንተ ሃይማኖት የሌላችሁት ትውልድ እስከመቼ ከናንተ ጋራ እኖራለሁ ።
እስከ ማዕዜኑ አትዔገሠክሙ እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ ።
አምጽእዎ ዝየ ኀቤየ ።
ወዲህ ወደኔ አምጡት አላቸው ።

፲፱ ወወሰድዎ ኀቤሁ ።
፲፱ ወደሱ ወሰዱት ።
ወሶበ ርእዮ ውእቱ ጋኔን ነጽሖ ሶቤሃ ውስተ ምድር
ያም ጋኔን ባየው ጊዜ ያንጊዜውን በምድር ጣለው ።
ወአስተራገጾ ። አራገጠው ።
ወአስወኖ ። አስለገው ፤

፳ ወተስእሎ እግዚእ ኢየሱስ ለአቡሁ ።
፳ ጌታ አባቱን ጠየቀው ፤
ወይቤሎ እማዕዜ ዘእኀዞ ።
ከምን ጊዜ ጀምሮ ነው የያዘው አለው ።
ወይቤሎ እምንዕሱ ።
ከትንሽነቱ ጀምሮ ነው አለው ።

፳፩ ወዘልፈ ያወድቆ ኀበ ጸድፍ ወውስተ እሳት ወማይ ።

፳፩ ዘወትር ከእሳትና ከውኃ ከገደል ይጥለዋል።
ከመ ይቅትሎ ። ሊገድለው ፤
ወባሕቱ በዘትክል ርድአኒ ።
ነገር ግን በሚቻልህ እርዳኝ ፤
ወመሐረኒ ። እዘንልኝ ፤

፳፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ እስመ ትቤ በዘትክል ርድአኒ እመ ትክል እሚነ ኵሉ ይትከሃል ለዘየአምን ።

፳፪ ጌታም አንተ እላመንክምና በተቻለህ እርዳኝ ትላለህ እንጂ ለሚያምንስ ሁሉ ይቻለዋል ፤
እንድም አንተ ባታምን በተቻለህ እርዳኝ ትላለህ
እንጂ ለሚያምን ግን ሁሉ ይቻለዋል ።

፳፫ ወጸርሐ አቡሁ ለውእቱ ወልድ ወይቤ እእምን ።

፳፫ የብላቴናውም አባት እምናለሁ ብሎ እስምቶ ተናገረ ።
ርድእ ለድካመ ሃይማኖትየ ።
ማመኔን እንዘው ማለት ሃይማኖቴን ፍጹም እድርግልኝ አለ ።

፳፬ ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ይትራወጽ ሰብእ ።

፳፬ ጌታም ሰዎች ሲራወጡ ባየ ጊዜ ።
ገሠፆ ለውእቱ ጋኔን ።
ያን ርኩስ መንፈስ ገሠፀው ።
ወይቤሎ ጋኔን እኩይ ወበሐም አነ እኤዝዘከ ትፃዕ እምኔሁ ።
አንተ ድዳ ደንቆሮውም ጋኔን ከሱ ትወጣ ዘንድ ፤
እኔ እዝዛለሁ አለው ።
ወኢትባእ እንከ ዳግመ ላዕሌሁ ።
ከእንግዲህም ወዲህ አትመለስበት ።

፳፭ ወአግዓሮ ብዙኃ ፤
፳፭ ብዙ አስጨነቀው ።
ወአስተራገፆ ወወፅአ
አራግጦት ወጣ ።
ወኮነ ከመ በድን
እንደ በድን ሆነ ።
እስከ ይብሉ ብዙኃን ሞተ
ብዙ ሰዎች ሞተ እስኪሉ ድረስ ።

፳፮ ወእኀዞ እግዚእ ኢየሱስ በእዴሁ ወአንሥኦ
፳፮ ጌታ በጁ ይዞ እነሣው ።
ወተንሥአ ፤ ተነሣ ።

፳፯ ወበዊኦሙ ቤተ ይቤልዎ አርዳኢሁ በባሕቲቶሙ በእፎ ስዕነ ንሕነ አውፅኦቶ ።

፳፯ ከቤት በገቡም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ እኛ ማውጣት እንደምን ተሣነን አሉት ።

፳፰ ወይቤሎሙ ዝንቱ ዘመድ ኢይከል እውፅኦቶ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት ።

፳፰ ይህ ዘመድ ያለ ጾም ያለ ጸሎት ያወጣ ዘንድ አይችልም አላቸው ።

፳፱ ወወፂአ ህየ ሖረ እንተ ገሊላ ።
፳፱ ከዚያም ወጥቶ ወደ ገሊላ ሄደ ።
ወኢፈቀደ ያእምርዎ ።
ሊያውቁት ግን አልወደደም ።

ዘከመ አቅደመ ነጊረ መዊቶቱ ፤

፴ ወመሐሮሙ ለአርዳኢሁ ማቴ ፲፯፥ ፳፩ ። ሉቃ ፱ ፥ ፳፪-፵፭ ።

፴ ደቀ መዛሙርቱን አስተማራቸው ፤
ወይቤሎሙ ሀለዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው ይግባዕ ውስተ እደ ሰብእ ኃጥአን ።
ክርስቶስ በሰው እጅ ይሰጥ ዘንድ አለው ፤
ወይቀትልዎ ፤ ይገድሉታል ።
ወይትነሣእ በሣልስት ዕለት ።
በሦስተኛውም ቀን ይነሣል ።

፴፩ ወኢያእመሩ ዘይቤሎሙ ።
፴፩ የነገራቸውን ግን አላወቁትም ።
ወይፈርህዎ ተስእሎቶ ሊጠይቁትም ፈሩ ።

በእንተ ትሕትና ወትዕግሥት ዘክርስቲያን ፤

፴፪ ወበጺሖ ቅፍርናሆም ወበዊአ ቤተ ይቤሎሙ ምንተኑ ሐለይክሙ በፍኖት በበይናቲክሙ ።

፴፫ ቅፍርናሆም ደርሰ በቤትም በገባ ጊዜ ከመንገድ ምን አስባችሁ ነበር ብሎ ጠየቃቸው ።

፴፬ ወአርመሙ ማቴ ፲፰ ፥ ፩ ሉቃ ፱ ፥ ፵፮
፴፬ ዝም አሉ ።
እስመ ተበሀሉ በበይናቲሆሙ በፍኖት መኑ እንጋ የዓቢ እምኔሆሙ ።
ከሳቸው ማናቸው እንዲበልጥ በመንገድ እርስ በርሳቸው ተነጋግረው ነበርና ።

፴፭ ወነበረ ወጸውዖሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ።
፴፭ ተቀምጦም አሥራ ሁለቱን ጠራቸው ።
ወይቤሎሙ ዘይፈቅድ ይኩን ሊቀ ለያትሕት ርእሶ ለኵሉ ።
በላይ ሊሆን የሚወድ ራሱን ለሁሉ ያዋርድ ።
ወይኩውን ላዕኩ ለኵሉ ።
ለሁሉም አገልጋይ ይሁን አላቸው ።

፴፮ ወነሥአ ሕፃነ ወዓቀሞ ማዕከሎሙ ።
፴፮ ሕፃኑን ወስዶ በመካከላቸው አቆመው ።
ወአንበሮ ውስተ ሕፅኑ ።
ባጠገቡ አኖረው ።
ወይቤሎሙ ዘተወክፈ ዘከመዝ ሕፃነ በስምየ ኪያየ ተወክፈ ።
እንደዚህ ሕፃን ያለውን በስሜ የተቀበለ እኔን ተቀበለኝ ።

፴፯ ወዘኒ ተወክፈ ኪያየ አኮ ኪያየ ባሕቲቶ ዘተወክፈ ዘእንበለ ዘፈነወኒ ።
፴፯ እኔንም የተቀበለ የላከኝን ነው እንጂ እኔን ብቻ የተቀበለ አይደለም ሐተታ በመንገድ ሳለ መኑ የዓቢ ተባብለዋል ከዚህ በኋላ ከቤት ገብቶ ቆይቶ በመንገድ ምን ተባብላችሁ ነበር አላቸው አወቀብን ብለው አርመሙ ዝም አሉ ምሳሌ ሕፃን ነገራቸው አንድም ከመንገድ መኑ የዓቢ ተባብለዋል ከቤት ገብቶ ከመንገድ ምን ተባብላችሁ ነበር አላቸው ማን ይበልጣል ተባብለን ነበር አሉት ምሳሌ ሕፃንን ነገራቸው አርመሙ አንድም ከመንገድ መኑ የዓቢ ተባብለዋል ከቤት ገብቶ ምሳሌ ሕፃንን ነገራቸው። አሳውቀብንም እንዳይሉ በዚያውስ ላይ በመንገድ ምን ተባብላችሁ ነበር አላቸው ።
አርመሙ ፤ ዝም አሉ ።

፴፰ ወአውሥኦ ዮሐንስ ወይቤሎ ሊቅ በዘር ኢነ እንዘ ያወጽእ አጋንንተ በስምከ ወከላዕናሁ ። ሉቃ ፱ ፥ ፵፱
፴፰ መምህር ሆይ በስምህ አጋንንትን ሲያወጣ አይተን የከለከልነው አለ ብሎ ዮሐንስ ተናገረ ።
እስመ ኢተለወነ ምስሌነ ።
ከኛ ጋራ አልተከተለህምና ማለት እንደኛ አላመነብህምና ፤

፴፱ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢትክልእዎ ፩ቆሮ ፲፪ ፥ ፫ ።

፴፱ ጌታም አትክልክሉት አላቸው ።
እስመ አልቦ ዘይገብር ኃይለ በስምየ ወይክል ፍጡነ አኂሥሞ ቃለ ሳዕሌየ ።
በስሜ ኃይል እየሠራ ፈጥኖ በኔ ላይ ክፉ ሊናገር አይችልምና ማለት እኔን ዕሩቅ ብእሲ እያለ በኔ ስም ተአምራት ማድረግ የሚቻለው የለምና ።

፵ እስመ እምከመ ኢኮነ ፀድውክሙ ቢጽክሙ ውእቱ ።

፵ ባለጋራችሁም ካልሆነ ወንድማችሁ ነው። ማለት እኔንም ዕሩቅ ብእሲ ካላለ ወንድማችሁ ነው ።
፵፩ ወዘአስተየክሙ ጽዋዓ ማይ ቊራር በስምየ እስመ አለ ክርስቶስ አንትሙ አማን እብለክሙ ኢየኃጕል ዕሤቶ ። ማቴ ፲ ፥ ፵፪ ።
፵፩ የክርስቶስ ወገን ናችሁና ብሎ በስሜ ጽዋ ውኃ ያጠጣችሁ ዋጋውን አያጣም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

ዘከመ ይደሉ አጥፍኦተ ዕቅፍት

፵፪ ወዘአስሐቶ ለ፩ እምእሉ ንኡሳን እለ የአምኑ ብየ ይኄይሶ ከመ ይዕሥሩ በክሣዱ ማኅረፀ አድግ ወያሥጥምዎ ውስተ ልጐተ ባሕር ። ማቴ ፲፰ ፥ ፮ ሉቃ ፲፯ ፥ ፪ ።
፵፪ በኔ ካመኑ አንዱን ያሳተ አህያ የሚፈጭ በትን የወፍጮ ድንጊያ ባንገቱ አስረው ከባሕር ጥልቅ ሊያሰጥሙት ይሻለዋል ።
፵፫ ወእመኒ እዴከ ታስሕተከ ምትራ ። ማቴ ፭ ፥ ፴ ፤ ፲፰ ፥ ፰ ፤
፵፫ እጅህም ብታስትሕ ቊረጣት ።
እስመ ይኄይሰከ ምቱረ እድ ትባእ ውስተ ሕይወት እምትባእ ምስለ ፪ኤሆን እደዊከ ውስተ እሳተ ገሃነም
፵፬ ኀበ እጼሁ ኢይነውም ወእሳቱ ዘኢይጠፍእ
፵፬ ትሉ ወደማይተኛበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም ሁለት እጅ ኑሮህ ከምትገባ እጅህ ተቆርጦ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃልና ።
፵፭ ወእመኒ እግርከ ታስሕተከ ምትራ ።
፵፭ እግርህም ብታስትህ ቊረጣት ።
እስመ ይኄይሰከ ሐንካስከ ትባእ ውስተ ሕይወት እምትባእ ምስስ ፪ሆን እገሪከ ውስተ እሳተ ገሃነም ።
፵፮ ኀበ ዕጼሁ ኢይነውም ወእሳቱ ኢይጠፍእ ። ኢሳ፡፷፮ ፥ ፳፬
፵፮ ትሉ ወደማይተኛበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነመ እሳት ሁለት እግር ኑሮህ ከምትገባ አንካሳ ሁነህ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃልና።
፵፯ ወእመኒ ዓይንከ ታስሕተከ ምልሐ ።
፵፯ ዓይንህም ብታስትህ አውጥተህ ጣላት ።
እስመ ይኄይሰከ ነቋረከ ትባዕ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር እምትባእ ምስለ ፪ሆን አዕይንቲከ ውስተ ገሃነም ዘእሳት ።
፵፰ ኀበ ዕጼሁ ኢይነውም ወእሳቱ ኢይጠፍዕ።

፵፯ ትሉ ወደማይተኛበት እሳቱም ወደማይ ጠፋበት ወደገሃነመ እሳት ሁለት ዓይን ኖሮህ ከምትገባ አንድ ዓይንህ ጠፍቶ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ብትገባ ይሻልሃልና ።

፵፰ እስመ ኵሉ በእሳት ይትሜላሕ ።
ዘሌዋውያን ፪ ፡ ፲፫ ።

፵፱ ሁሉ በእሳት ይጣፍጣል አኮን ወኵሉ ዘይጠባሕ ይትሜላሕ በጼው ።
የሚሠዋውን ሁሉ በጨው ያጣፍጡታል ።

፶ ሠናይ ውእቱ ጼው ።

፶ ጨው መልካም ነው ።
ወእመሰ ጼው ለስሐ በምንት እንከ ይቄስምዎ ።
ማቴ ፭ ፡ ፲፫ ። ሉቃ ፲፬ ፡ ፴፬ ።
ጨው ግን አልጫ ከሆነ በምን ያጣፍጡታል ።
ጼወ ርከቡ በበይናቲከሙ ።
እናንተ በናንተ ጼው አግኙ ።
ወተሰነአው ። ተስማሙ ።
አንድም እስመ ኵሉ በእሳት ይትሜላህ ብለህ መልስ
ሥራውን ሁሉ በሃይማኖት ይሠሩታል ።
ወኵሉ ዘይጠባሕ ፤ ሥራውን ሁሉ በፍቅር ይሠሩታል ።
ሠናይ ውእቱ ጼው ፤ ፍቅር መልካም ነው ።
ወእመሰ ጼው ለስሐ ።
ፍቅር ከሌለ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ በምን ይሠሩታል
ጼወ ርከቡ ፤ ፍቅርን ያዙ ።
ወተሰነአው ብሎ ገልጠው ተስማሙ ።

ዘከመ ተግሕሠ ኢየሱስ እም ኢየሩሳሌም ።

ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወተንሢአ እምህየ ሖረ ብሔረ ይሁዳ እንተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ። ማቴ ፲፱ ፡ ፩ ።

፩ ከዚያ ተነሥቶ በዮርዳኖስ ማዶ ይሁዳ ከሚ ባል አገር ሄደ ።
ወሖሩ ምስሌሁ ሕዝብ ።
ሕዝቡም ከሱ ጋራ ሄዱ ።
ወመሐሮሙ በከመ ያስምድ ።
እንደለመደ አስተማራቸው ።

ዘከመ ኢይደሉ ኅዲገ ብእሲት ወእውስቦ ካልዕት ።

፪ ወመጽኡ ካዕበ ፈሪሳውያን ወተሰእልዎ ።

፪ ዳግመኛ ፈሪሳውያን መጥተው ጠየቁት ።
እንዘ ይብሉ ቦኑ ይከውንኑ ለብእሲ ኅዲገ ብእሲቱ ።
ለሰውም ሚስቱን መፍታት ይገባዋልን ብለው ፤
እንዘ ያሜክርዎ ፤ ሲፈትኑት ።

፫ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ምንትኑ አዘዘከሙ ሙሴ ።

፫ ሙሴ ምን አዝዟችሁ ነበር ብሎ መለሰላቸው ።

፬ ወይቤልዎ አዘዘነ ሙሴ ንጽሕፍ ላቲ መጽ ሐፈ ኅዳጋቲሃ ወንድኃራ ። ዘዳ ፳ ፡ ፴፩ ።

፬ ሙሴ የፍችዋን መጽሐፍ ጽፎ ሰጥቶ ይፍ ታት ብሎ አዞናል አሉት ።

፭ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ በከመ እከየ ልብከሙ ወሀበከሙ ሙሴ ዘንተ ትእ ዛዘ ትድኃሩ አንስቲያከሙ ።

፭ ጌታም ሙሴ እንደልቡናችሁ ክፋት ሚስ ቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ አዘዛችሁ ብሎ መለሰላቸው ።

፮ ወእምፍጥረትሰ ተባዕተ ወአንስተ ገብረ እግ ዚአብሔር ።

፮ ከፍጥረት መጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ተባ ዕትና አንስት አደረገ ።

፯ ወበእንተ ዝንቱ የኃድግ ብእሲ አባሁ ወእሞ ወይትልዋ ለብእሲቱ ። ዘፍ ፪ ፡ ፳፬ ማቴ ፲፱ ፡ ፭ ፩ቆሮ ፮ ፡ ፲ ኤፌ ፭ ፡ ፴፩ ።

፯ ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል ማለት ከሚስቱ ጋራ አንድ ይሆናል ።
ወይከውኑ ፪ሆሙ ፩ደ ሥጋ ፩ ቆሮ ፮ ፡ ፲፮ ።

፰ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ።
ናሁኬ ኢኮኑ ፪ተ ፤ እነሆ ሁለትም አይደሉም ።

፰ አላ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ ፤
አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ።

፱ ዘእግዚአብሔር እንከ አስተፃመረ ሰብእ ኢይፍልጥ ።

፱ እግዚአብሔር ያገናኘውን ሰው አይለይ ። ሐተታ፡ማቴዎስ ፈሪሳውያን ጠየቁት ይላል ማርቆስ እሉ ጠየቃቸው አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ይከውኑ ለብእሲ ይድኃር ብእሲቶ በኵሉ ዘአበሰት ሎቱ ቢሉት ኢያ ንበብክሙኑ ዘውስተ ኦሪት ዘከማ ፈጠሮሙ ተባዕተ ወአንስተ ገብሮሙ ብእሴ ወብእሲተ ረሰዮሙ ። ወበእንተዝ የኃድግ ብእሲ አባሁ ወእሞ ወይተልዋ ለብእሲቱ ይላቸዋል ፤ ለምንትኑ እንከ አዘዘነ ሙሴ ይሉታል ፤ ምንተ እንከ አዘዘከሙ ይላቸዋል ፤ ሙሴሰ እዘዘነ ንጽሐፍ ላቲ መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ወን ድኃራ ይሉታል፤እሱም ሙሴሰ አዘዘከሙ በከመ እከየ ልብከሙ ትድኃሩ አንስቲያከሙ ወእምፍጥ ረትሰ አኮ ከመዝ ዘእግዚአብሐር አስተፃመረ ሰብእ ኢይፍልጥ ይላቸዋል ፤ አንድም ይከውኑ ለብእሲ ቢሉት ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ ሰብእ ኢይፍልጥ ይላቸዋል ፤ ለምንት አዘዘነ ሙሴ ይሉታል ፤ ምንትኑ አዘዘከሙ ይላቸዋል ፤ ሙሴሰ አዘዘነ ንጽሐፍ ላቲ መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ወንድኃራ ይሉታል ፤ እሱም ሙሴሰ አዘዘከሙ በከመ እከየ ልብከሙ ትድኃሩ አንስቲያከሙ ወእምፍጥረትሰ አኮ ከመዝ ብሎ ኢያ

ንበብክሙኑ ዘውስተ ኦሪት ዘከመ ቀዲሙ ፈጠሮሙ ተባዕተ ወአንስተ ገብሮሙ ብእሲ ወብእሲተ ረሰዮሙ ወበእንተዝ የኃድግ ብእሲ አባሁ ወእሞ ፤ ወይተልዋ ለብእሲቱ ወይከውኑ ፪ሆሙ ፩ደ ሥጋ ወናሁ ኢኮኑ ፪ኤተ አላ ፩ዱ ሥጋ ን ሙንቱ ይላቸዋል ፤ አንድም ይከውኖሁ ቢሉት ምንትኑ አዘዘክሙ ሙሴ ይላቸዋል ። ሙሴስ አዘዘን ይሉታል ፤ ሙሴስ አዘዘክሙ በከመ እከየ ልብክሙ እምፍጥትሰ ብሎ ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ ሰብእ ኢይፍልጥ ይላቸዋል ።

፲ ወበቤት ካዕበ ተስእልዎ አርዳኢሁ በእንተ ዝንቱ ።

፲ ስለዚህ ነገር ደቀ መዛሙርቱ ሁለተኛ በቤት ጠየቁት ።

፲፩ ወይቤሎሙ ዘደኃረ ብእሲቶ ወሖረ ካልዕተ ዘመወ ላዕሌሃ ።

፲፩ ሚስቱን የፈታ ሌላይቱንም ያገባ ሰሰነባት።

፲፪ ወእንተሂ ደኃራ ምታ ወሖረት ካልዓ ዘመወት ።

፲፪ ባሏ የፈታትም ሌላ ወንድ ብታገባ ሰሰነች እላቸው ።

ዘከመ ባረኮሙ ኢየሱስ ለሕፃናት ።

፲፫ ወአምጽኡ ኀቤሁ ሕፃናተ ይግሥሦሙ ።

፲፫ ሕፃናትን ይዳስሳቸው ወደሱ አመጧቸው ።
ወገሠጽዎሙ አርዳኢሁ ለእለ አምጽእዎሙ ።
ደቀ መዛሙርቱ ግን ያመጧቸውን ተቆጧቸው ።

፲፬ ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ተምዓ ።
ጌታም አይቶ ተቆጣ ።

፲፬ ወይቤሎሙ ኅድጉ ሕፃናተ ይምጽኡ ኀቤየ ወኢትክልእዎሙ ሕፃናትን ወደኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው ።
እስመ ለከመዝ እሉ ይእቲ መንግሥተ እግዚአብሔር መንግሥተ እግዚአብሔር እንደዚህ ላሉ ናትና ።

፲፭ አማን እብለክሙ ዘኢተቀበላ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ከመ ሕፃን ኢይበውዓ ።

፲፭ መንግሥተ እግዚአብሔርን እንደ ሕፃን ያልተቀበላት አይገባትም ብየ በውነት እነግራችኋለው ።

፲፮ ወአንበሮሙ ውስተ ሕፅኑ ወባረኮሙ ።
፲፮ ባጠገቡ አኑሮ ባረካቸው ።
ወወደየ እደዊሁ ዲቤሆሙ ።
እጁንም ጫነባቸው ።

በእንተ ወሬዛ ባዕል ።

፲፯ ወእንዘ የሐውር በፍኖት መጽአ ፩ዱ ብእሲ ወሰገደ ሎቱ ።
ማቴ ፲፱ ፥ ፲፮ ሉቃ ፲፰ ፥ ፲፰ ።

፲፯ በመንገድ ሲሄድ አንድ ሰው መጥቶ ሰገደለት ።
ወይቤሎ ሊቅ ኄር ምንተ እግበር ከመ እረስ ሕይወተ ዘለዓለም ቸር መምህር ሆይ የዘላለምን ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ሳደርግ አለው ።

፲፰ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ምንተ ትብለኒ ኄር ።

፲፰ ጌታም ምን ቸር ትለኛለህ ፤
አልቦ ኄር ዘእንበለ ፩ዱ እግዚአብሔር ፤
ያላንድ እግዚአብሔር ቸር የለም አለው ።

፲፱ ተአምር ትእዛዛተ ። ዘፀ ፳ ፥ ፲፫
፲፱ ትእዛዛትን ታውቃለህ ፤
ኢትሑር ብእሲተ ብእሲ ።
ወደጎልማሳ ሚስት አትሂድ ፤
ኢትቅትል ነፍሰ ፤ ነፍስ አትግደል ።
ኢትሥርቅ ፤ አትሥረቅ
ኢትኩን ስምዓ በሐሰት ፤
በሐሰት አትመስክር ።
ኢትሂድ ፤ አትቀማ ።
አክብር አባከ ወእመከ ፤
አባት እናትህን አክብር ።

፳ ወአውሥአ ወይቤሎ ሊቅ ዘንተ ኵሎ ዓቀብኩ እምንዕስየ ።

፳ መምህር ሆይ ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሮ ጠብቄዋለሁ ብሎ መለሰ ።

፳፩ ወነጸሮ እግዚእ ኢየሱስ ።
፳፩ ጌታም ወደሱ ተመለከተ ።
ወአፍቀሮ ፤ ወደደውም ።
ወይቤሎ አሐተ ፈቀድከ ፍጹመ ትኩን አሐቲ ተርፈተከ ።
ፍጹም ልትሆን ከወደደህስ አንዲት ቀርታሃለች ።
፳፪ ሑር ሢጥ ኵሎ ዘብከ ወሀብ ለነዳያን ።
፳፪ ሂደህ ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ ።
ወትረክብ መዝገበ በሰማያት ፤
በሰማይ ገንዘብ ታገኛለህ ።
ወጹር መስቀለ ሞትከ ወነዓ ትልወኒ ።
የምትሞትበትንም መስቀል ተሸከመህ መጥተህ ተከተለኝ ።
ወተከዘ በእንተ ዝንቱ ነገር ወሖረ ትኩዞ ።
ስለዚህ ነገር አዝኖ ተከዞም ሄደ ፤
እስመ ብዙኅ ጥሪቱ ፤
ገንዘቡ ብዙ ነበርና ።
ወነጸሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ።
ጌታም ወደ ደቀ መዛሙርቱ አየ ።

፳፫ ወይቤሎሙ እፎ ዕፁብ ለዘቦ ንዋይ በዊአ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፳፫ ገንዘብ ያለው ሰው ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መግባት እንደምን ጭንቅ ይሆን አላቸው ።

፳፬ ወአንከሩ አርዳኢሁ ዘንተ ነገረ ።

፳፬ ደቀ መዛሙርቱም ይህን ነገር አደነቁ ። ወካዕበ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ደቂቅየ እፎ ዕጹብ ለዘቦ ንዋይ በዊእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ።
ዳግመኛም ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ልጆቼ ለባለጸጎች ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት እንደምን ጭንቅ ይሆንባቸዋል አላቸው ።

፳፭ ይቀልል ይኅልፍ ገመል እንተ ቀፈረ ሐፅ እምባዕል ይባዕ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፳፭ ባለ ጸጋ ከብቱን ጨርሶ መጥውቶ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ከሚገባ ገመል ከንጭነቱ በደጋኑና በጅማቱ መካከል ቢያልፍ ይቀላል ። ይህስ ያልፋል ብሎ ደጋኑ ብስ አለው በዚያ ቢያልፍ ይቀላል ሲል ነው ። ሐተታ ማቴዎስ ስቍረተ መርፍዕ ይላል ከዚህ ማርቆስ ቀፈረ ሐፅ አለ እንደምን ነው አይለያይም ቢሉ አይለያይም የሁለት ቀን ትምህርት የልሳን መለያየት ነው ።

፳፮ ወፈድፋደ አንከሩ ወተባሀሉ በበይናቲሆሙ መኑ እንከ ይክል ድኂነ ።

፳፮ እጅግም አድንቀው እንግዲህ መዳን የሚቻለው ማነው ተባባሉ ።

፳፯ ወነጸሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ሀንበ ሰብእ ኢይትከሃል ዝ ።

፳፯ ጌታ አይቷቸው ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም ።
ወበኀበ እግዚአብሔርሰ ኵሉ ይትከሃል ።
በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል አላቸው ።

በእንተ ዕሤቶሙ ለእለ

ይተልውዎ ለኢየሱስ ።

፳፰ ወአኀዘ ጴጥሮስ ይቤሎ ናሁኬ ንሕነ ኀደግነ ኵሎ ወተለውናከ ። ማቴ ፲፱ ፡ ፳፯ ። ሉቃ ፲፰ ፡ ፳፰ ።

፳፰ ጴጥሮስም እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከትለንሃል ይለው ጀመር ።

፳፱ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ አልቦ ዘየኀድግ አብያተ ወአኃወ አበ ወእመ ብእሲተ ወውሉደ ወገራውሀ በእንቲአየ ወበእንተ ወንጌልየ ።

ዘኢይትዓሠይ ምዕተ ምክዕቢተ በዝንቱ ዓለም አብያተ ወአኃወ ወአኃተ አበ ወእመ ወገራውሃ በስደት ።

፳፱ ጌታም እኅቶቹንና ወንድሞቹን አባቱንና እናቱንም ልጆቹንና ሚስቱን እርሻውንም በለኔ ስለ ወንጌልም በስደት የተወ ፤ ቤቶችን እኅቶችንና ወንድሞችንም አባትና እናትንም እርሻንም በዚህ ዓለም መቶ ዕፅፍ የማያገኝ የለም ብሎ መለሰላቸው ።

፴ ወበዓለምስ ዘይመጽእ ሕይወተ ዘለዓለም ።

፴ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወትን ያገኛል ።

፴፩ ወብዙኃን ቀደምት ይከውኑ ደኃርተ ። ማቴ ፲፱ ፡ ፴ ።

፴፩ ነገር ግን ብዙ የፊተኞች የኋለኞችን ይሆናሉ ።
ወደኃርትኒ ይከውኑ ቀድመ ።
የኋለኞችም ወደፊት ይሆናሉ ።

በእንተ ካልዕ ትንቢት ዘሕማማት ።

፴፪ ወበፍኖት እንዘ የዓርግ ኢየሩሳሌም ። ሉቃ ፲ ፡ ፰ ፤ ፴ ፡ ፩ ።

፴፪ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በመንገድ ፤
ይቀድሞሙ እግዚእ ኢየሱስ ፤
ጌታም በፊታቸው ነበር ፤
ደንገጹ ፤ ደነገጡ ።
ወእለሂ ይተልውዎ ፈርሁ ፤
የተከተሉትም ፈሩ ።
ወነሥኦሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ፤
አሥራ ሁለቱንም ይዟቸው ሄደ ።
ወአኀዘ ይንግሮሙ ዘሀለዎ ይርከቦ ፤
ይደርስበት ዘንድ ያለውንም ይነግራቸው ጀመር ።

፴፫ ወይቤሎሙ ናሁ ነዓርግ ኢየሩሳሌም ።

፴፫ እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን ።
ወይእኀዝዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ።
ሊቃነ ካህናትና ጸሐፍት ክርስቶስን ይይዙታል ።

፴፬ ወይኬንንዎ በሞት ፤

፴፬ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል ።
ወይሜጥውዎ ለአሕዛብ ፤
ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል ።
ወይሣለቁ ላዕሌሁ ።
ይዘብቱበታል ።
ወይዌርቅዎ ፤ ይተፋበታል ።
ወይቀሥፍዎ ፤ ይገርፉታል ።
ወይቀትልዎ ፤ ይገሉታል ።
ወይትነሣእ በሣልስት ዕለት ።
በሦስተኛውም ቀን ይነሣል ።

በእንተ ገሥፆ ትዝሕርት ዘደቂቀ ዘብዴዎስ ።

፴፭ ወእንዘ የሐውሩ ምስሌሁ ያዕቆብ ወዮሐንስ ፪ሆሙ ደቂቀ ዘብዴዎስ ይቤልዎ ሊቅ ንፈቅድ ትግበር ለነ ዘስአልናከ ።

፴፭ ሁለቱም የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ ከሱ ጋራ ሲሄዱ የለመንህን ልታደርግልን እንወዳለን አሉት ። ሐተታ ማቴዎስ እናታቸው ሄዳ ተናገረች ይላል ማርቆስ እላቸው ተናገሩ አለ ፤ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው እሷ ሄዳ ተናግራለች ማርቆስ እላቸው ተናገሩ ማለቱ አብረው ሄደው መናገራቸውን ሲያይ

ዛሬ እማላጅ የሰደደ ሰው አብሮ ሄዶ እንዲናገር እንድም ነገር እንደ ማርቆስ ነው፡ ፊት እሳቸው ተናግረዋል እሞታለሁ እሰቀላለሁ ብላቸው ሹመት ይለምኑኛል ብሎ ሳይመልሳቸው ቀረ ። ለኛስ አልመለሰልንም በዚያ በዘመድሽ ዕወቂበት አንች ሄደሽ ተናገሪልን ብለዋት እሷ ሄዳ ተናግራለች ይህን ተካፍለው ጽፈዋል ።

፴፮ ወይቤሎሙ ምንተ ትፈቅዱ እግበር ለክሙ
፴፮ ምን ሳደርግላችሁ ትወዳላችሁ አላቸው ።
፴፯ ወይቤልዎ ሀበነ ንንበር ፩ድነ በየማንከ ወ፩ድነ በጸጋምከ ስውስተ ስብሐቲከ ።
፴፯ በጌትነትህ አንዳችን በቀኝህ አንዳችን በግራህ እንቀመጥ ዘንድ ስጠን አሉት ።
፴፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢተአምሩ ዘትሰአሉ ።

፴፰ ጌታም የምትለምኑትን ዐታውቁም አላቸው፡ ትክሉኑ ሰትየ ጽዋዕ ዘአነ እሰቲ እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጡ ዘንድ ትችላላችሁን ።
ወጥምቀትየኒ ዘአነ እጠመቅ ትጠመቁኑ ።
እኔ የምጠመቀውንስ ጥምቀት ትጠመቁ ዘንድ ትችላላችሁን አላቸው ።
፴፱ ወይቤልዎ እወ ንክል ።
፴፱ እንችላለን አሉት ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ጽዋዕየሰ ዘአነ እሰቲ ትሰትዩ ።
የምጠጣውንስ ጽዋ ትጠጣላችሁ ፤
ወጥምቀትየኒ ዘአነ እጠመቅ ትጠመቁ ፤
የምጠመቀውንም ጥምቀት ትጠመቃላችሁ ፤
፵ ወነቢረሰ በየማንየ ወበፀጋምየ አኮ አነ ዘእሁበክሙ ።

፵ በቀኝና በግራ መቀመጥን ግን እኔ እምሰጣችሁ አይደለሁም ።
አላ ለካልዓን አስተዳለወ ሎሙ አቡየ ዘበሰማያት ።
የሰማይ አባቴ ለሌሎች አዘጋጅቶላቸዋል እንጂ ።
፵፩ ወሰሚዖሙ ፲ቱ ተምዑ ዲበ ፪ቱ አኃው ያዕቆብ ወዮሐንስ ።

፵፩ ዐሥሩ ሰምተው በሁለቱ ወንድማማች በያዕቆብና በዮሐንስ ተቆጡ ።

፵፪ ወጸውዖሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ኢተአምሩኑ ከመ መላእክቲሆሙ ለአሕዛብ ይኴንንዎሙ ሉቃ ፳፪ ፡ ፳፭ ።
፵፪ ጌታም ጠርቶ አሕዛብን አለቆቹ እንዲፈርዱባቸው ታላላቆችም እንዲፈርዱባቸው አታውቁም አላቸው ።
፵፫ ወአኮሙሰ አኮ ከማሁ ፤
፵፫ ለናንተስ እንዲህ አይሆንም አላ ዘይፈቅድ እምኔክሙ ይኩን ሊቀ ይኩንክሙ ገብረ ።
ከናንተ በላይ ሊሆን የሚወድ ተገዥ ይሁናችሁ ።

፵፬ ወዘይፈቅድ እምኔክሙ ይኩን ዓቢየ ይኩንክሙ ላዕከ ።

፵፬ ከናንተ ታላቅ ሊሆን የወደደ አገልጋይ ይሁናችሁ እንጂ ።

፵፭ እስመ ወልደ ዕጓለ እመሕያውኒ ኢመጽአ ከመ ይትለአክዎ ዘእንበለ ዳእሙ ከመ ይትለአክ ።
፵፭ የሰው ልጅ ክርስቶስ ስንኳ ሊያገለግል ነው እንጂ ሊያገለግሉት አልመጣምና ።
ወከመ ይቤዝዎሙ ለብዙኃን በነፍሱ ።
በነፍሱም ለውጥ ብዙዎችን ሊያድናቸው ነው እንጂ ።

በእንተ ዕውር ወልደ በርጤሜዎስ ።

፵፮ ወቦአ ኢያሪኮ ። ማቴ ፳፥፳፱ ሉቃ ፲፰፥፴፭
፵፮ ወደ ኢያሪኮ ገባ ።
ወሶበ ወፅአ እምኢያሪኮ ወአርዳኢሁኒ ምስሌሁ ወሰብእኒ ብዙኅ ።
ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ሰዎችም ከሱ ጋራ ሁነው ከኢያሪኮም በወጣ ጊዜ ።
ሀሎ ጤሜዎስ በርጤሜዎስ ዕውር ይነብር ውስተ ፍኖት ወይስእል ።
ዕውሩ ጤሜዎስ የበርጤሜዎስ ልጅ ከመንገድ ተቀምጦ ይለምን ነበር ። ሐተታ በር በዕብራይስጥ ልሳን ልጅ ማለት ነው ፤ ዕውር የዕውር ልጅ ማለት ነው ።

፵፯ ወሰሚዖ ከመ ኢየሱስ ናዝራዊ የኀልፍ ከልሐ ወይቤ ተማሀለኒ ኢየሱስ ወልደ ዳዊት ።

፵፯ የናዝሬቱ ኢየሱስ እንደሆነ ሰምቶ የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ ማረኝ ብሎ አሰምቶ ተናገረ ።
፵፰ ወገሠጽዎ ብዙኃን ከመ ያርምም ።
፵፰ ብዙ ሰዎች ዝም ይል ዘንድ ተቆጡት ።
ወአፈድፈደ ከሊሐ ።
እሱ ግን ጩኸትን አበዛ ።
ወይቤ ወልደ ዳዊት ተሣሃለኒ ።
የዳዊት ልጅ ማረኝ አለ ።
፵፱ ወቆመ እግዚእ ኢየሱስ ወአዘዘ ይጸውዕዎ ።
፵፱ ጌታም ቆሞ ጥሩት አለ ።
ወጸውዕዎ ለእውቱ ዕውር ።
ያንም ዕውር ጠሩት ።
ወይቤልዎ ተአመን ወተንሥእ ይጼውዓክ ሊቅ ።
መምር ይጠራሀልና እምነህ ተነሣ አሉት ።
፶ ወተንሥአ ወገደፈ ልብሶ ።
፶ ልብሱን ጥሎ ተነሣ ።
ወለብሰ ልብሶ ወመጽአ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ።
ልብሱንም ለብሶ ወደ ጌታ መጣ ። ሐተታ መምር ይጠራሃልአሉት እፈፍ ብሎ ሲነሣ ልብሱ ወደቀበት እንሥቶ ለብሶ ይሄዳል ፤ እንድም የዘወትር ተርታ ልብስና ከሰው የሚደርስበት ደሀና ልብስ አለው የዘወትሩን ትቶ ደሀናውን ልብስ ለብሶ ሄደ ።

፶፩ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ምንተ ትፈቅድ እግበር ለከ ።

፶፩ ጌታም መለሰ ምን ላደርግልህ ትወዳለህ አለው ።

ወይቤሎ ውእቱ ዕውር ረቡኒ ከመ እርአይ ።
መምር ሆይ አይ ዘንድ ነው አለው ።

፶፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ሑር ሃይማኖትከ አሕየወተከ ።

፶፪ ጌታም ሂድ ሃይማኖትህ አድናሃል አለው ።

ወርእየ ሶቤሃ ።   ያን ጊዜውንም አየ ።
ወተለዎ በፍኖት ፤   በመንገድም ተከተለው ።

ዘከመ ቦአ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም

ምዕራፍ ፲፩

፩ ወአልጺቆሙ ኢየሩሳሌም ኀበ ቤተ ፋጌ ወቢታንያ እንተ ገቦ ደብረ ዘይት ፈነው ፪ተ እምአርዳኢሁ ። ማቴ ፳፩ ፡ ፩ ሉቃ ፲፱ ፡ ፳፱ ።

፩ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ወደ ደብረ ዘይት አጠገብ ወደ ቢታንያና ወደ ቤተ ፋጌ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ ።

፪ ወይቤሎሙ ሑሩ ውስተ ሀገር እንተ ቅድሜክሙ ።

፪ በፊታችሁ ወዳለ አገር ሂዱ አላቸው ።

ወበዊአክሙ ሶቤሃ ትረክቡ ዕዋለ አድግ ዕሡረ ዘኢተጽዕኖ ሰብእ ።
በገባችሁም ጊዜ ሰው ያልተቀመጠበት ያህያ ግል ግል ታስሮ ታገኛላችሁ ።
ፍትሕዎ ወአምጽእዎ ሊተ ።
ፈታችሁ አምጡልኝ ።

፫ ወለእመቦ ዘይቤለክሙ ምንተ ትገብሩ በሉ እግዚኡ ይፈቅዶ ።

፫ ምን ታደርጋላችሁ ያላችሁም ሰው ቢኖር ጌታ ይሻዋል በሉ ። ሐተታ ማቴዎስ ዕድግትንም ዕዋልንም ይጽፋል ማርቆስ ዕዋልን ብቻ ጻፈ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ሁለት ናቸው ማርቆስ አንድ ማለቱ ለመናገር ከበቃ ብሎ ነው ፤ አንድም ማቴዎስ መምህረ አሕዛብ ወሕዝብ ነውና የሁለቱንም ምሳሌ ተናገረ ማርቆስ ግን መምህረ አሕዛብ ነው እንጂ መምህረ ሕዝብ አይደለምና የአሕዛብን ምሳሌ ዕዋልን ብቻ ለይቶ ተናገረ ።
ወሶቤሃ ይፌንወክሙ ዝየ ።
ያን ጊዜውንም ወደዚህ ይልካችኋል ።

፬ ወሖሩ ወረከቡ ዕዋለ ዕሡረ ኀበ አንቀጽ ውስተ ፍኖት ።

፬ ሄደውም ግልገሉን ከመንገድ አጠገብ ባደባባይ ታሥሮ አገኙት ።
ወፈትሕዎ ፤   ፈቱትም ።

፭ ወይቤልዎሙ እለ ይቀውሙ ህየ ምንተ ትገብሩ ዘትፈትሑ ።

፭ ቆመው ያሉትም ውርንጫውን የምትፈቱት ምን ታደርጋላችሁ አሏቸው ።

፮ ወይቤልዎሙ በከመ አዘዞሙ እግዚእ ኢየሱስ ።

፮ ጌታ እንዳዘዛቸውም ነገሯቸው ወኀደግዎሙ ተዋቸውም ።

፯ ወወሰድዎ ለዕዋል ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ። ዮሐ ፲፪ ፡ ፲፬ ።

፯ ግልገሉንም ወደጌታ አመጡት ።
ወረኀኑ አልባሲሆሙ ላዕሌሁ ወአጽአንዎ ።
ልብሳቸውንም ጎዝጉዘው አስቀመጡት ።

፰ ወብዙኃን እለ ነጸፉ ቆጽለ መቲሮሙ እምዕፀው ።

፰ ቅጠል ከዛፍ እየቆረጡ የጎዘጎዙም ብዙ ናቸው ።
ወቦ እለ ነጸፉ አልባሲሆሙ ውስተ ፍኖት ።
ልብሳቸውንም ከመንገድ የጐዘጐዙ አሉ ።

፱ እለኒ ይመርሑ ወእለኒ ይተልው ይኬልሁ ወይብሉ ሆሣዕና ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ።

፱ በፊትም በኋላም ይሄዱ የነበሩት በእግዚአብሔር ስም የሚመጣው የተባረከ ሆሣዕና ነው ብለው አሰምተው ተናገሩ ።

፲ ወቡርክት እንተ ትመጽእ መንግሥት በስመ እግዚአብሔር እንተ አቡነ ዳዊት ። መዝ ፻፲፯ ፡ ፳፮ ማቴ ፳፩ ፡ ፱ ሉቃ ፲፱ ፡ ፴፰ ።

፲ በእግዚአብሔር ስም የምትመጣ ያባታችን የዳዊት መንግሥትም የተባረከች ናት ። ሐተታ ዳዊት በትንቢት ያከናወናት ቡርክት እንተ ትመጽእ መንግሥት ያላት ማለት ነው ሆሣዕና በአርያም ።
በሰማይ መድኃኒት መባል ይገባዋል አሉ ።

፲፩ ወቦአ እግዚእ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ኀበ ቤተ መቅደስ ። ማቴ ፳፩ ፡ ፲ ።

፲፩ ጌታም ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ቤተ መቅደስ ገባ ።
ወርአይዎ ኵሉ ሕዝብ ።
ሕዝቡም ሁሉ አዩት ።
ወሶበ መስየ ሖረ ቢታንያ ምስለ ፲ቱ ወ፪ቱ ።
በመሸም ጊዜ ወደቢታንያ ካሥራሁለቱ ጋራ ወጣ ።

በእንተ በለስ ዘተረግመት ።

፲፪ ወበሳኒታ ሶበ ወጽአ እምቢታንያ ርህበ ። ማቴ ፳፩ ፡ ፲፱

፲፪ በነጋውም ከቢታንያ በወጣ ጊዜ ተራበ።

፲፫ ወርእየ ዕፀ በለስ እምርኁቅ ዘባቲ ቈፅል ።

፲፫ በሩቅም ቅጠል ያባት በለስ አየ ።

ወሖረ ይርአይ እመቦ ዘይረክብ በውስቴታ ።
በሷ ፍሬ ያገኝ እንደሆነ ሊያይ ሄደ ።
ወበጺሖ ኀቤሃ አልቦ ዘረከበ ዘእንበለ ቈጽል ባሕቲቱ
ወደርሷም በደረሰ ጊዜ ከቅጠል ብቻ በቀር ያገኘው
የለም ።
እስመ ኢኮነ ጊዜሁ ለበለስ ።
የበለስ ወራት አልነበረምና ።

፲፬ ወአውሥአ ወይቤላ አልቦ ፍሬ ዘይበልዕ
እምኔኪ ለዓለም ።

፲፬ ለዘለዓለም ካንቺ ፍሬ የሚበላ አይኑር አላት
ወሰምዑ አርዳኢሁ ።
ደቀ መዛሙርቱም ሰሙ ።

በእንተ አለ ያረዙቡ ቤተ መቅደስ

፲፭ ወበጽሐ ኢየሩሳሌም ወቦአ ቤተ መቅደሰ ።
፲፭ ኢየሩሳሌም ደረሰ ወደ ቤተ መቅደስም ገባ
ወአኀዘ ይሰድድ እለ ይሣየጡ በምኵራብ ።
በምኵራብ ዋጋ የሚያደርጉትን ያስወጣ ጀመረ ።
ወገፍትዓ ማዕዳቲሆሙ ለመወልጣን ።
የለዋጮችንም ማዕዳቸውን ገለበጠ ።
ወመናብርቲሆሙ ለእለ ይሠይጡ ርግበ ።
ርግብ የሚሸጡትንም ወንበር ፤

፲፮ ወኢኀደገ ከመ ኢያብኡ ንዋየ ውስተ ምኵ
ራብ ።

፲፮ ወደ ምኵራብ ገንዘብ እንዲያገቡ ከለከለ ።
፲፯ ወመሀሮሙ ወይቤሎሙ አኮኑ ጽሑፍ ዘይ
ብል ቤትየሰ ቤተ ጸሎት ይኩን ለኵሉ አሕዛብ ።
ኢሳ ፶፮ ፡ ፯ ኤር ፯ ፡ ፲፩ ።
፲፯ ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ይሁን
የሚል ጽሑፍ ያለ አይደለምን ብሎ አስተማራቸው ።
ወአንትሙሰ ረሰይክምዎ በዓተ ፈያት ወሠረቅት ።
እናንተ ግን የሌቦችና የወንበዴች ዋሻ አደረጋችሁት፤
የገበያውን መፈታት ማቴዎስ እሑድ ይላል ማርቆስ
ሰኞ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ፤
ደገኛውን ገበያ እሑድ ፈቶታል ጥቃቅኑን ገበያ ሰኞ
ፈቶታል ።
፲፰ ወሰምዑ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ወኃ
ሠሡ እንተ ኀበ ይቀትልዎ ።
፲፰ ሊቃነ ካህናትና ጸሐፍት ሰምተው የሚ
ገድሉበትን ምክንያት ይፈልጉ ጀመር ።
ወፈርህዎ ፤ ፈሩት ።
እስመ ኵሉ ሕዝብ ያነክሩ ምሕሮቶ ።
ሕዝቡ ሁሉ ትምርቱን ያደንቁ ነበርና ።
፲፱ ወሶበ መስየ ወጽአ አፍአ እምሀገር ።
፲፱ በመሸም ጊዜ ከከተማው ወደ ውጪ ወጣ ።

በእንተ ትወክልት ኀበ እምላክ

፳ ወበጊዜ ነግህ ኀልፈ ሰዱ ምልዕልተ ጽግብ እምሥርዋ ።
፳ ወበጊዜ ነግህ ረከብዋ ለይእቲ በለስ
ይብሰት እምሥርዋ ።

፳ በነጋው ሲመለሱ ያችን በለስ ከሥርዋ
ደርቃ አገኙዋት ፤ ሐተታ ይብሰተ በለሰን ማቴዎስ
ሰኞ ይላል ማርቆስ ማክሰኞ አለ እንደምን ነው አይ
ጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ሰኞ
ማታ ረገሟት መድረቅ ጀምራለች ማክሰኞ ተነ
ቃቅላ ወድቃለች መድረቅ የጀመረችበትን ሲያይ
ማቴዎስ ሰኞ አለ ተነቃቅላ የወደቀችበትን ሲያይ
ማርቆስ ማክሰኞ አለ ፤ አንድም የደረቀችም የወደ
ቀችም ሰኞ ነው መሸቶባቸው ሳያይዋት ሄደዋል
ማክሰኞ ቢመለሱ ተነቃቅላ ወድቃ አይተዋታል
ማቴዎስ የደረቀችበትን ሲያይ ሰኞ አለ ማርቆስ
ያዩበትን ሲያይ ማክሰኞ አለ ።

፳፩ ወተዘከረ ጴጥሮስ ቃሎ ለእግዚእ ኢየሱስ
ወይቤሎ ሊቅ ነያ እንታክቲ በለስ እንተ ረገምካ
የብሰት ።

፳፩ ጴጥሮስ አስቦ መምህር ሆይ እነሆ ያች
የረገምካት በለስ ደረቀች አለው ።

፳፪ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ
ለእመ ኮነ ውስቴትክሙ ሃይማኖተ እግዚአብሔር
ማቴ ፳፩ ፡ ፳፩ ።

፳፪ ጌታ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው
እግዚአብሔርን ማመን በናንተ ቢኖር ።

፳፫ አማን እብለክሙ ለእመ ትብልዎ ለዝንቱ
ደብር ተንሥእ ወተወረው ውስተ ባሕር ወኢና
ፈቅሙ በልብክሙ ወተአመንክሙ ይከውን ዘነበ
ብክሙ ወትረክቡ ።

፳፫ እውነት እላችኋለሁ ይህን ተራራ ተነሥተህ
ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት በልቡናችሁም ባት
ጠራጠሩ ብታምኑ እንደተናገራችሁት ሆኖ ታገኛ
ላችሁ ።

፳፬ ወበእንተዝ ዕብለክሙ ኵሎ ዘጸለይክሙ
ወሰአልክሙ እንዘ ትትአመኑ ከመ ትረክቡ ወይ
ከውነክሙ ። ማቴ ፯ ፡ ፯ ፤ ፳፩ ፡ ፳፪ ።
፳፬ ስለዚህ እምላካችሁ የጸለያችሁትን የለመ
ናችሁትንም ሁሉ እንድታገኙ እንዲያደርግላችሁ
እነግራችኋለሁ ።

፳፭ ወሶበሂ ትጼልዩ ኅድጉ ለቢጽክሙ ዘቦ
ሐየስክምዎሙ ።

፳፭ በምትጸልዩበትም ጊዜ ወንድሞቻችሁን
የነቀፋችሁባቸውን ይቅር በሉ ።
ከመ ይኅድግ ለክሙ አቡክሙ ዘበሰማያት አበሳክሙ፤
ሰማያዊ አባታችሁ በደላችሁን ይቅር ይላችሁ ዘንድ

፳፮ ወእመሰ አንትሙ ኢኃደግሙ አቡክሙኒ
ሰማያዊ ኢየኃድግ ለክሙ ።

፳፮ እናንተ ግን ይቅር ካላላችሁ ሰማያዊ አባ
ታችሁም ይቅር አይላችሁም ።

በእንተ ተስእሎት ዘዮሐንስ መጥምቅ

፳፯ ወሖረ ካዕበ ኢየሩሳሌም ። ሉቃ ፳ ፡ ፩

፳፯ ሁለተኛ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ።
እንዘ ያንሶሱ በምኵራብ መጽኡ ኀቤሁ ሊቃነ ካህናት ።
በምኵራብ ሲመላለስ ጻፎችና ሊቃነ ካህናት ወደሱ መጡ ።
ወረበናት ።
ሽማግሎችም ።

፳፰ ወይቤልዎ በመባሕተ መኑ ትገብር ዘንተ ፤
፳፰ ይህን በማን ሥልጣን ታደርጋለሀ ።
ወመኑ አብሐከ ትግበር ዘንተ ።
ይህን ታድርግ ዘንድ ማን አሰናበተሀ አሉት ።

፳፱ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እነኒ እሴእለክሙ አሐተ ነገረ ።

፳፱ ጌታም እኔም አንድ ነገር እጠይቃችኋለሁ ።
ወንግሩኒ ፤ እናንተም ንገሩኝ ።
እነኒ እየድዓክሙ ፤ እኔም እነግራችኋለሁ ።
በመባሕተ መኑ እገብር ከመዝ ።
ይህን የማደርገው በማንም ሥልጣን እንደሆነ ።

፴ ጥምቀቱ ለዮሐንስ እም አይቴኑ ።
፴ የዮሐንስ ጥምቀት ከወዴት ናት ።
እምሰማይኑ አው እምሰብእ ።
ከሰማይን ነው ወይስ ከሰውን ነው አላቸው ።
አይድኡኒ ፤ መልሱልኝ ።

፴፩ ወተባሐሉ በበይናቲሆሙ ለእመ ንብሎ እምሰማይ ይብለነ ለምንት ኢአመንክምዎ ።

፴፩ እርስበሳቸውም አሰቡ ከሰማይ ብንለው ምነው አላመናችሁበት ይለናል ።

፴፪ ወስእመኒ ንብሎ እምሰብእ ንፈርሆሙ ለሕዝብ ።

፴፪ ከሰው ብንለውም ሕዝቡን እንፈራቸዋለን
እስመ ኵሎሙ ከመ ነቢይ ይሬእይዎ ለዮሐንስ ።
ሁሉም ዮሐንስን እንደ ነቢይ ያዩት ነበርና ።

፴፫ ወተሰጥውዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ወይቤልዎ ኢነአምር ።

፴፫ እናውቅም ብለው ለጌታ መለሱለት ።
ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ፤
ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ እንኒ ኢይነግረክሙ በመባሕተ መኑ እገብር ከመዝ ።
እኔም በማንም ሥልጣን ይህን እንዳደርግ አልነግራችሁም አላቸው ።

በእንተ እኩያን ዐቀብተ ወይን

ምዕራፍ ፲፪

፩ ወአኀዘ ይመስል ሎሙ ። ኢሳ፭፥ ፩ ኤር፥ ፪ ፡ ፳፩ ማቴ ፳፩ ፡ ፴፫ ሉቃ ፳ ፡ ፱ ።

፩ ይመስልላቸው ጀመረ ።
ይቤሎሙ ብእሲ ተከለ ዓጸደ ወይን ።
ሰው ወይን ተከለ ።
ወጸቆና ፤ ቅጥር ቀጠረለት ።
ወአክረየ ምክያደ ፤
መጥመቂያም አስማሰለት ።
ወሐነጸ ማኅፈደ ውስቴቱ ።
በሱም ግንብ ሠራ ።
ወሤመ ሎቱ ዓቀብተ ወነገደ ።
ጠባቂም ሹሞ ሄደ ።

፪ ወፈነወ ገብሮ ኀበ ዓቀብተ ወይን በጊዜሁ ያምጽእ ሎቱ እምፍሬ ወይኑ ።
፪ ከወይኑም ፍሬ ያመጣለት ዘንድ ባሪያውን በጊዜው ወደ ጠባቆች ላከ ።
፫ ወእኀዝዎ ፡
፫ ያዙት ።
ወቀሠፍዎ ፤ ገረፉት ።
ወፈነውዎ ዕራቆ ፤
ባዶውንም ሰደዱት ።

፬ ወካዕበ ፈነወ ኀቤሆሙ ካልዓኒ ገብሮ ።
፬ ደግሞ ሌላውንም ባሪያውንም ወደሳቸው ላከ።
ወኪያሁኒ ወገርዎ ፤ እሱንም ደበደቡት ።
ወኰርዕዎ ፤ መቱትም ።
ወፈነውዎ አኅሲሮሙ ፤
አዋርደውም ሰደዱት ።

፭ ወፈነወ ሣልሳየኒ ገብሮ ፤
፭ ሦስተኛውንም ባሪያውን ላከ ፤ ሐተታ ዮሐንስ መጥምቅ ነው ።
ወኪያሁኒ ቀተልዎ ፤
እሱንም ገደሉት ።
ወፈነወ ባዕዳነኒ ብዙኃነ ።
ሌሎችንም ብዙዎችን ላከ ።
ቦ ዘቀሠፉ ፤ የገረፉት አለ ።
ወቦ ዘቀተሉ ፤ የገደሉትም አለ ።
፮ ወቦቱ ፩ዱ ወልድ ዘያፈቅር ።
፮ የሚወደው አንድ ልጅም ነበረው ።
ወፈነዎ ኀቤሆሙ ድኅረ ኵሉ እንዘ ይብል የኀፍርዎ ለወልድየ ።
ከሁሉ በኋላ ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከ ።
፯ ወይቤሉ ዓቀብት ዝንቱ ውእቱ ወራሲሁ
፯ ጠባቆቹም እነሆ ወራሹ ይህ ነው ።
ንዑ ንቅትሎ ። ኑ እንግደለው ።
ወንርከብ ርስቶ ፤

ርስቱንም እንውረሰው አሉ ።

፰ ወአኀዝዎ ወአውፅእዎ አፍአ አምአፀጸ ወይን ወቀተልዎ ።

፰ ይዘውም ከወይኑ ቦታ ውጭ አውጥተው ገደሉት ።

፱ ምንተ እንከ ይሬስዮሙ በዓለ ወይን ።
፱ የወይኑ ባለቤት ምን ያደርጋቸዋል ።
አኮኑ ይመጽእ ወይቀትሎሙ ለእልኩቱ ዓቀብት ።
መጥቶ ጠባቆችን ይገድላቸው የለምን ።
ወይሁብ ወይኖ ለካልዓን ።
ወይኑንም ለሌላ ጠባቆች ያስጠብቃል ።

፲ ወዘኒ ኢያንበብክሙኑ ውስተ መጽሐፍ እብን እንተ ዘመነንዋ ነደቅት ይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማዕዘንት ፡ መዝ ፻፲፯ ፡ ፳፪ ኢሳ፡ ፳፰ ፡ ፲፮ ማቴ፡ ፳፩ ፡ ፵፪ ግብ ፬ ፡ ፲፩ ሮሜ ፱ ፡ ፴፫ ፩ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፯ ።
፲ እናንት የናቁት ድንጋይ የማዕዘን ራስ ሆነች ያለውን ከመጽሐፍ አላሰባችሁምን ።
፲፩ እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ ።
፲፩ ይህችም ከእግዚአብሔር ሆነች ።
ወነካር ይእቲ ለአዕይንቲነ ።
ለዓይናችንም ድንቅ ናት ።
፲፪ ወፈቀዱ የአኀዝዎ ።
፲፪ ሊይዙትም ወደዱ ።
ወፈርህዎሙ ለሕዝብ ።
ሕዝቡንም ፈሩ ።
ወአእመሩ ከመ በእንቲአሆሙ ይቤ ዘንተ እምሳለ ።
ይህንም ምሳሌ ስለርሳቸው እንደተናገረው ዐወቁ ።
ወኀደግዎ ወሖሩ ።
ትተውትም ሄዱ ።

ዘከመ አመከርዎ ለኢየሱስ በእንተ ውሂበ ዲናር

፲፫ ወፈነዉ ኀቤሁ ፈሪሳውያን ምስለ ሰብአ ሄሮድስ ከመ ያስሕትዎ በቃሉ ። ማቴ ፳፪ ፡ ፲፭ ሉቃ፡ ፳፡ ፳ ።
፲፫ በነገሩ ሊያስቱት ፈሪሳውያን ከሄሮድስ ሰዎች ጋራ ወደሱ ላኩ ።
፲፬ ወመጽኡ ኀቤሁ ወይቤልዎ ሊቅ ነአምር ከመ ጻድቅ አንተ ።
፲፬ ወደሱም መጥተው መምር ሆይ እውነተኛ እንደሆንክ እናውቃለን ።
ወኢየኃዝነከ መኑሂ ።
ማንንም ማንን እንዳታፍር ።
ወኢታደሉ ለገጸ ሰብእ ።
ለሰው ፊትም እንዳታደላ ።
በጽድቅ ትሜህር ፍኖተ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርን መንገድ በውነት እንድታስተምር እናውቃለን ።

፲፬ ይከውነሁ ነሀብ ጸባሕተ ዲናር ለንጉሥ ።
፲፬ ለቄሣር ግብር መስጠት ይገባልን ።
እው አልቦ ።
ወይም አይገባም አሉት ።

፲፭ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ጕሕሉቶሙ ለምንት ታሜክሩኒ ።

፲፭ ጌታም ሽንገላቸውን ዐውቆባቸው ለምን ትፈትኑኛላችሁ ።
አምጽኡ ዲናረ ወእርእዩኒ ።
ዲናሩንም አምጥታችሁ አሳዩኝ አላቸው ።
፲፮ ወአምጽኡ ሎቱ ። ሮሜ ፲፫ ፡ ፯ ።
፲፮ አመጡለት ።
ወይቤሎሙ ዘመኑ መልከዑ ወመጽሐፉ ።
ጽፈቱስ መልኩስ የማነው አላቸው ።
ወይቤልዎ ዘንጉሥ ።
የቄሣር ነው አሉት ።
ሀቡ ዘንጉሥ ለንጉሥ ።
የቄሣርን ለቄሣር ስጡ ።
ወዘእግዚአብሔር ግበሩ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ።
ወአንከርዎ ፤ አደነቁት ።

በእንተ ሰዱቃውያን ወትንሣኤ ሙታን ።

፲፰ ወመጽኡ ኀቤሁ ሰዱቃውያን እለ ይብሉ አልቦ ትንሣኤ ሙታን ። ማቴ ፳፪፡ ፳፫ ሉቃ፡ ፳፡፳፯ ።
፲፰ የሙታን ትንሣኤ የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደሱ መጡ ።
ወተስእልዎ ፤ ጠየቁት ።
፲፱ ወይቤልዎ ሊቅ ሙሴ ጸሐፈ ለነ ወለእመቦ ዘሞተ እኁሁ ወኀደገ ብእሲቶ ወአልቦቱ ውሉድ እኁሁ ያውስባ ለብእሲቱ ። ዘፀ ፳፭ ፡ ፭ ።
፲፱ ወንድሙ ልጅ ሳይወልድ ሚስቱን ትቶ የሞተ እንደሆነ ወንድሙ ሚስቱን ያግባት ።
ወያቅም ዘርዓ ለእኁሁ ።
ለወንድሙ ልጅ ይተካ ብሎ ሙሴ ጽፎልናል ።
፳ ሀለው ኀቤነ ፯ቱ አኀው ።
፳ ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ ።
ወአውሰበ ዘይልሕቅ ብእሲተ ።
ታላቁ ሚስት አገባ ።
ወሞተ እንዘ አልቦ ውሉድ ።
ልጅ ሳይወልድ ሞተ ።
፳፩ ወአውሰባ ካልዑኒ ።
፳፩ ሁለተኛውም አገባት ።
ወሞተ እንዘ አልቦ ውሉድ ።
ልጅ ሳይወልድ ሞተ ።
ወሣልሱኒ ከማሁ ።
ሦስተኛውም እንዲሁ ።

፳፪ ወ፯ሆሙ እውሰብዋ ፤
፳፪ ሰባቱም አገቧት ።
ወኢኀደጉ ውሉደ ።
ልጅ ግን አልነበራቸውም ።
ወድኅረ ኵሎሙ ሞተት ይእቲ ብእሲት ።
ከሁሉም በኋላ ያች ሞተች ።

፳፫ ወእመሰ የሐይው ምውታን ለመኑ እምኔሆሙ ትከውኖ ብእሲተ ።

፳፫ ሙታን በተነሡ ጊዜ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች ።
እስመ ፯ሆሙ አውሰብዋ ፤
ሰባቱም አግብተዋታልና ።

፳፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፳፬ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ አኮኑ በእንተ ዝንቱ ስሕትክሙ በኢያእምሮ መጻሕፍት ።
መጻሕፍትን ባለማወቅ ።
በኢኃይለ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ኃይልንም ባለማወቅ በደላችሁ ።

፳፭ እመሰ የሐይው ምውታን ኢያወስቡ ወኢይትዋሰቡ ።

፳፭ ሙታን በተነሡ ጊዜ አያገቡም አይጋቡም። አላ ከመ መላእክተ እግዚአብሔር ይከውኑ እሙንቱ በሰማያት ።
በሰማይ እንዳሉ መላእክት ይሆናሉ እንጂ ።

፳፮ ወከመሰ የሐይው ምውታን ኢያንበብክሙኑ በውስተ መጽሐፈ ሙሴ ዘይቤሎ እግዚአብሔር በኀበ ዕፀ ጳጦስ ዘፀ ፫ ፡ ፮ ማቴ ፳፪ ፡ ፴፪ ።

፳፮ ምውታንማ እንዲነሱ በቁጥቋጦው ዘንድ እግዚአብሔር እንደነገረው የሙሴን መጽሐፍ አላነበባችሁምን ።
እንዘ ይብል አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ።
አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ
አምላከ አብርሃም ፤
የአብርሃም አምላክ ።
ወአምላከ ይስሐቅ ፤
የይስሐቅ አምላክ ።
ወአምላከ ያዕቆብ ፤
የያዕቆብ አምላክ ።

፳፯ ኢኮነኬ አምላከ ምውታን ።
፳፯ የሙታን አምላክ አይደለም ።
አላ አምላከ ሕያዋን ውእቱ ፤
የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ ።
ወእንትሙሰ ብዙኃ ትጌግዩ ፤
እናንተስ ብዙ ትስታላችሁ ።

በእንተ ቀዳማዊ ትእዛዝ

፳፰ ወመጽአ ፩ዱ ጸሐፊ ሰሚዖ ከመ ተኃሠሥዎ ወሶበ ርእየ ከመ ሠናየ ተሠጥዎሙ ። ማቴ ፳፪ ፡ ፴፭ ።
እንደ ተከራከሩት በሰማ ጊዜ መልካም እንደመለሰላቸው ባየ ጊዜ አንድ ጸሐፊ ወደሱ መጣ ።
ወተሰእሎ ወይቤሎ ዓይኑ ትእዛዝ ቀዳሚት እምኵሉ ከሁሉም የምትቀድም ትእዛዝ ማንኛይቱ ናት ብሎ ጠየቀው ።

፳፱ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
ዘዳ ፮ ፡ ፬ ።

፳፱ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ ዛቲ ይእቲ ቀዳሚት እምኵሉ ትእዛዝ ።
ከትእዛዝ ሁሉ የምትቀድም ይህች ናት ።
ስማዕ እስራኤል እግዚአብሔር አምላክከ ፩ዱ ውእቱ እግዚአብሔር ።
እስራኤል ሆይ አምላክህ እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር እንደሆነ ስማ ።

፴ ወአፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ልብከ ።
፴ አምላክህ እግዚአብሔርንም በልብህ ሁሉ ውደደው ።
ወበኵሉ ነፍስከ ፡ ወበኵሉ ሕሊናከ ።
በነፍስህም ሁሉ ፡ በሕሊናህም ሁሉ ።
ወበኵሉ ኃይልከ ።
በኃይልህም ሁሉ ።
ዛቲ ይእቲ ትእዛዝ ቀዳሚት እምኵሉ ።
ከሁሉም የምትቀድም ትእዛዝ ይህች ናት ።
፴፩ ወካልዕታሂ እንተ ትመስላ አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ ። ዘሌ ፲፱ ፡ ፲፰ ማቴ ፳፪ ፡ ፴፱ ሮሜ ፲፫ ፡ ፱ ገላ ፭ ፡ ፲፬ ያዕ ፪ ፡ ፰ ።
፴፩ ሁለተኛይቱም የምትመስላት ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ ናት ።
ወዘየዓቢ እምእላንቱ ትእዛዛት አልቦ ።
ከነዚህ ትእዛዞች የሚበልጥ የለም ።
፴፪ ወይቤሎ ውእቱ ጸሐፊ ሠናየ ትቤ ሊቅ ።
፴፪ ያም ጸሐፊ መምህር ሆይ መልካም ተናገርኽ አለው ።
እማን ፩ዱ ውእቱ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር በእውነት አንድ ነው ።
ወአልቦ ባዕድ ዘእንበሌሁ ።
ከሱም በቀር ሌላ የለም ።
፴፫ ወከመ ታፍቅሮ በኵሉ ልብከ ።
፴፫ በልብህ ሁሉ ትወደው ዘንድ ።
ወበኵሉ ነፍስከ ።
በነፍስህም ሁሉ ።
ወበኵሉ ሕሊናከ ፤ በሕሊናህም ሁሉ ።
ወበኵሉ ኃይልከ ፤ በኃይልህም ሁሉ ።

ወከመ ታፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ ።
ባልንጀራህን እንደ ራስህ ብትወድ ።
ወዝንቱ ይኄይስ እምኵሉ መባዕ ወመሥዋዕት ።
ከመሥዋዕትና ከመባዕም ሁሉ ይህ ይሻላል ።

፴፬ ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ጠቢብ ውእቱ ይቤሎ ኢኮንከ ርሑቀ እመንግሥተ እግዚአብሔር ።

፴፬ ጌታም ብልህ እንደሆነ አይቶ ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቅህ አይደለህም አለው ።
ወእልቦ እንከ ዘተሀበለ ይሰአሎ ።
ከዚህም ወዲያ ሊጠይቀው የደፈረ የለም ።

በእንተ ማበያቱ ወልደ ዳዊት

፴፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይሜህሮሙ በምኵራብ እፎ ይብሉ ጸሐፍት ወልደ ዳዊት ውእቱ ክርስቶስ ።
፴፭ ጌታም በምኵራብ ሲያስተምራቸው ጸፎች ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው እንደምን ይላል ብሎ ጠየቃቸው ።
፴፮ ወለሊሁሰ ዳዊት ይቤ በመንፈስ ቅዱስ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ እስከ አገብኦሙ ለጸላእትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ ።
መዝ ፻፱ ፣ ፩ ማቴ ፳፪ ፣ ፵፬ ሉቃ ፳ ፣ ፵፪
፴፮ እሱ ግን ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን ከእግርህ መርገጫ በታች እስከ አገባቸው በቀኜ ተቀመጥ አለው ብሏል ።
፴፯ ወለሊሁ ዳዊት እግዚእየ ይቤሎ እፎ እንከ ይከውኖ ወልደ ።
፴፯ እሱ ዳዊት ጌታዬ ያለው እንደምን ልጁ ይሆናል ።
ወኵሎ ሕዝብ ሠናየ ያጸምዕዎ ። ማቴ ፳፫ ፣ ፩ ሉቃ ፲፩ ፣ ፵፫ ።
ሕዝቡም ሁሉ ደስ ብሏቸው ይሰሙት ነበር ።

በእንተ መደልዋን ጸሐፍት

፴፰ ወይቤሎሙ እንዘ ይሜህሮሙ ዑቁ ወተገኃሡ እምጸሐፍት እለ ይፈቅዱ ያንሶስዉ ተላቢሶሙ
፴፰ ሲያስተምራቸው ተላብሰው መመላለስን ከሚወዱ ከፈሪሳውያን ተጠበቁ ተለዩም አላቸው
ወይትአምኅዎሙ በምሥያጣት ።
በገበያም ምርቃትን የሚወዱ ።
፴፱ ወነበረ ፍጽም በውስተ አዕዋዳት ።
፴፱ ባደባባይም ፊት ለፊት መቀመጥን የሚወዱ ።
ወርእሰ ምርፋቃት በውስተ ምስሐት ።
በምሳ ጊዜ በራስጌ መቀመጥን ።
፵ እለ ይውህጥዎሙ ለአብያተ መበለታት ።
፵ የድሆችን ቤት የሚበሉባቸው ።
ወይትሜየኑ በነዋህ ጸሎቶሙ ።
በረጅም ጸሎታቸውም የሚተነኰሉ ።
እሉ ይረክቡ ዘየዓቢ ኰነኔ ።
እኒህ የሚበልጥ ፍርድ ይቀበላሉ ።

በእንተ ዘከመ ወደሳ ለመበለት ነዳይት በውሂቦተ ጸሪቅ ።

፵፩ ወነበረ እግዚእ ኢየሱስ ቅሩበ ምኵራብ እንጸረ ሙዳየ ምጽዋት ይርአይ ሰብአ ዘያበውኡ ጸሪቀ ወይወድዩ ውስተ ሙዳየ ምጽዋት ። ሉቃ ፳፩ ፣ ፩ ።

፵፩ መባ የሚሰጡትን በሳጥንም የሚያኖሩትን ያይ ዘንድ ጌታ በዕቃ ቤቱ አፋዛኙ ባለ በምኵራብ ደጅ ተቀምጦ ሳለ ፤
ወብዙኃን አብዕልት እለ አብኡ ብዙኃ ።
ብዙ ባለጠጎችም ብዙ አገቡ ።
፵፪ ወመጽአት አሐቲ ብእሲት ነዳይት መበለት
፵፪ አንዲት ድኃ ሴት መጣች ።
ወአብአት ፪ተ ጸሪቀ ።
ሁለት ጸራይቅም አገባች ፤
ዘይብልዎ ቆንደራጢስ ፤
ቆንደራጢስ የሚሉት ፤
ሐተታ ሁለት ጸራይቅ ያለውን አንድ አድርጎ ቆንደራጢስ አለ ሁለቱን ተረን አንድ ቀመት ሁለቱን ቀመት አንድ ድሪም እንደማለት ፤
አንድም የሙርኝ እንጀራ አንድም ዝብስ ብርት ነው በሞረድ ሲሞርዱት ጊዜ ይረግፋል ያን ሰብሰበው ለእንጀራ ይሸጡታልና ፤

፵፫ ወጸውዖሙ ለአርዳኢሁ ።
፵፫ ደቀ መዛሙርቱንም ጠራቸው ወይቤሎሙ አማን እብለክሙ ከመ ዛቲ ነዳይት መበለት አብዝኃት አብአ እምኵሎሙ እለ አብኡ ውስተ ሙዳየ ምጽዋት ።
በመባው ሣጥን ካገቡ ሁሉ ይህች ሴት አብዝታ እንደሰጠች በውነት እነግራችኋለሁ ።
፵፬ እስመ ኵሎሙ እለ አብኡ እምተረፎሙ አብኡ ።

፵፬ ያቀረቡት ሁሉ ትርፋቸውን አግብተዋልና ።
ወይእቲሰ እምተፅናሳ ኵሎ ዘባቲ አብአት ኵሎ መንበርታ ፤
ይህች ግን በድኅነት ሳለች ያላትን ሁሉ አገባች ። ሐተታ እኒያ ከቤታቸው ሄደው እንደ ገና ተድላ የሚያደርጉ የሚበሉ የሚጠጡናቸውና ፤ እሷ ግን የሚያ የምትውል ናትና ፤ ይህች ሴት የኀጥአን ነፍስ እኒያ የጻድቃን ምሳሌ ፤ ጻድቃን ምን አለብን ብለው ተዘልለው ይኖራሉ ፤ የኃጥአን ነፍስ ግን አላበጀሁም ብላ በታዘን ሲታለቅስ ትኖራለች ። ጻድቃን ነን ከሚሉ ከኒያ ይልቅ ኃጥእት ነን ነፍስ አብዝታ ሥራ ሠርታለች ብዬ እነግራችኋለሁ ።

በአንተ ንስቶተ ቤተ መቅደስ
ወኢየሩሳሌም ።

ምዕራፍ ፲፫

፩ ወወፂአ እምኵራብ ይቤሎ ፩ዱ እምአርዳኢሁ ሊቅ ርኢ ምንተ ይመስል ንድቁ ወዕበዪሁ ማቴ፡ ፳፬ ፡ ፩ ።

፩ ከምኵራብ በወጣም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ መምህር ሆይ ድንጊያውንና ሕንጻውን ምን ይመስላል እየው አለው ።

፪ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ። ሉቃ፡፲፫ ፡ ፴፬
ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፮ ።
፪ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ ትሬኢኑ ዘንተ ኵሎ ንድቀ ዓቢየ ።
ይህን ታላቅ ሥራ ታያለህን ።
ኢይትኃደግ ዝየ እብን ዲበ እብን ዘኢይትነሰት ።
የማይፈርስ ሆኖ ድንጊያ በደንጊጊያ ላይ አይቀርም ።
፫ ወእንዘ ይነብር ውስተ ደብረ ዘይት አንጻረ ምኵራብ ተስአልዎ በባሕቲቶሙ ጴጥሮስ ወያዕቆብ ወእንድርያስ ።
፫ በደብረ ዘይት በምኵራብ አንጻር ተቀምጦ ሳለ ያዕቆብና ጴጥሮስ እንድርያስም ለብቻቸው ጠየቁት ።
፬ ወይቤልዎ ንግረነ ማዕዜ ይከውን ዝንቱ ።
፬ ይህስ የሚደረገው መቼ ነው ንገረን ።
ወምንት ትእምርቱ አመ ይከውን ዝንቱ ኵሉ ።
ይህስ ሁሉ በተደረገ ጊዜ ምልክቱ ምንድር ነው አሉት ።
፭ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ። ኤፌ ፭ ፡ ፮
፪ ተሰ፡ ፪ ፡ ፫ ።
፭ ጌታም መለሰ ።
ወአኀዘ ይበሎሙ ዑቁ ኢያስሕቱክሙ ።
እንዳያስቷችሁ እስተውሉ ይላቸውም ጀመረ ።
፮ እስመ ብዙኃን ይመጽኡ በስምየ እንዘ ይብሉ አነ ውእቱ ክርስቶስ ።
፮ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ ብዙ ስዎች በኔ ስም ይመጣሉና ።
ወያስሕትዎሙ ለብዙኃን ።
ብዙ ስዎችንም ያስቷቸዋል ።
፯ ወአመ ሰማዕክሙ አፅባዕተ ወድምፀ ጸባኢት ዑቁ ኢትደንግፁ ።
፯ ሰልፍና የስልፍንም ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ እንዳትደነግጡ አስተውሉ ።
እስመ ሀለዎ ይኩን ዝንቱ ።
ይህ ይሆን ዘንድ አለውና ።
ወባሕቱ አኮ ሶቤሃ ዘየኃልቅ ።
ነገር ግን ያን ጊዜ የሚፈጸም አይደለም ።
፰ ወይትነሣእ ሕዝብ ዲበ ሕዝብ ።
፰ ሕዝቡም በሕዝቡ ላይ ይነሣል ።
ወነገሥት ዲበ ነገሥት ።
ነገሥት በነገሥት ላይ ።
ወይከውን ድልቅልቅ በበበሔሩ ።
በየሀገሩም መናወጥ ይሆናል ።
ወይመጽእ ረኃብ ።
ረኃብም ይመጣል ።
ወዝንቱ ቀዳሚሁ ለጻዕር ።
ይህም የጻዕር መጀመሪያ ነው ።

፱ ወአንትሙሰ ዑቁ ርእሰክሙ ።
፱ እናንተ ግን ለራሳችሁ አስተውሉ ።
ወይወስዱክሙ አዕዋዳተ ።
ወደ ዐደባባይ ይወስዷችኋል ።
ወይቀሥፉክሙ በመኳርብት ።
በምኵራብም ይገርፏችኋል ።
ወይትባጽሑክሙ ኀበ መላእክት ወነገሥት በእንቲአየ ።
ስለኔ ወዳለቆችም ወደ ነገሥታትም ያደርሷችኋል ።
ከመ ይኩን ስምዓ ላዕሌሆሙ ምስክር ሊሆንባቸው ።

፲ ወለኵሎሙ አሕዛብ ያደሉ ይቀድሙ ይስብክዋ ለወንጌል ።
፲ ለአሕዛብም ሁሉ አስቀድሞ ወንጌልን ሊያስተምሯቸው ይገባል ።
፲፩ ወሶበሂ ያበጽሑክሙ ኢትቅድሙ ተሐልዩ ዘትብሉ ወዘትነብቡ ። ማቴ፡፲ ፡ ፲፱ ሉቃ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ፤ ፳፩ ፡ ፲፬
፲፩ ባደረሷችሁም ጊዜ አስቀድማችሁ የምትናገሩትን አታስቡ ።
ዘእንበበክሙ ሶቤሃ ንቡ ።
ያን ጊዜ ያናገራችሁን ተናገሩ ።
እስመ ኢኮንክሙ አንትሙ ዘትነብቡ ።
የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁምና ።
ዘእንበለ መንፈስ ቅዱስ ።
መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ ።
፲፪ ወያገብእ እኁው እኁሁ ለሞት ።
፲፪ ወንድም ወንድሙን ለሞት አሳልፎ ይሰጠዋል ።
ወአብ ወልዶ ፤ አባትም ልጁን ።
ወውሉድ ይትነሥኡ ላዕለ አዝማዲሆሙ ።
ልጆች ባባቶቻቸው ላይ ይነሣሉ ።
ወይቀትልዎሙ ፤ ይገድሏቸዋል ።
፲፫ ወትከውኑ ጽሉአነ በኀበ ኵሉ በእንተ ስምየ ።
፲፫ ስለኔ ስም በሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ።
ወዘሰ አዝለፈ ትዕግሥቶ ውእቱ ይድኅን ።
እስከ ፍጻሜ የታገሠ ግን ይድናል ።
፲፬ ወሶበ ርኢክሙ ኃጕለ ሰሙስና ዘይቤ ዳንኤል ነቢይ ዘይቀውም ውስተ መካን ቅዱስ ዘያነብብ ለይለቡ ።

፲፬ ነቢዩ ዳንኤል የተናገረውን የመፍረሱን ርኩሰት ባያችሁ ጊዜ በቅዱስ ቦታ የቆመው አንባቢው ያስተውል ።
ውእተ አሚረ እለ ውስተ ይሁዳ ይጕዩ ውስተ አድባር
ያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደተራራ ይሽሹ ።

፲፭ ወዘኒ ውስተ ናኅስ ኢይረድ ውስተ ቤት ።
፲፭ በሰገነትም ያለ ወደቤት አይውረድ ።
ወኢይባእ ይንሣእ ዘኮነ እምቤት ።
ከቤቱም እንዳች ይወስድ ዘንድ አይግባ ።

፲፮ ወዘኒ ገዳመ ሀሎ ኢይትመየጥ ድኅሬሁ ከመ ይንሣእ ልብሶ ።

፲፮ በዱርም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ ።

፲፯ ወባሕቱ እሌ ሎን ለፅንሳት ወለእለ የሐፅና በውእቱ መዋዕል ።

፲፯ ነገር ግን ለፀነሱ በዚያም ወራት ለሚያ ሳድጉ ወዮላቸው ።

፲፰ ወጸልዩ ከመ ኢይኩን ጕያክሙ በክረምት።
፲፰ ሽሽታችሁም በክረምት እንዳይሆን እመ ልከቱ ።

፲፱ እስመ ይከውን ይእተ አሚረ ዓቢይ ሕማም ዘእምእመ ኮነ ዓለም ኢኮነ ከማሁ ።

፲፱ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እንደሱ ተደርጎ የማያውቅ ታላቅ መከራ ይሆናልና ።
ወእምከመ ፈጠረ እግዚእብሔር ።
እግዚአብሔርም ከፈጠረው ፍጥረት ጀምሮ ።
ወኢይከውንሂ ፤
ከእንግዲህም ወዲህ የማይደረግ ።

፳ ወሶበ እኮ ዘአሕፀሮን እግዚአብሔር ለእማንቱ መዋዕል እምኢድኅነ ኵሉ ዘሥጋ ።
፳ እግዚአብሔርስ ዘመኑን ባያሳጥረው ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር ።
ወባሕቱ በእንተ ኅሩያኒሁ እለ ኃረየ እግዚአብሔር
እግዚአብሔር የሐፀራ እማንቱ መዋዕል ።
ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ መረጣቸው እኒያ ወራቶች ያጥራሉ ።

፳፩ ወይእተ አሚረ እመቦ ዘይቤለክሙ ነዋ ዝየ ሁሎ ክርስቶስ ። ማቴ፡ ፳፬ ፡ ፳፫ ሉቃ ፲፯፡ ፳፫ ፳፬ ፡ ፰ ።

፳፩ ያን ጊዜም ክርስቶስ ከዚህ ነው ።
ወነዋ ከሐከ ።
ወይም ከዚያ ነው ያላችሁ ሰው ቢኖር ።
ኢትእመኑ ፤ አትመኑ ።

፳፪ እስመ ይመጽኡ ሐሳውያነ መሲሕ ።
፳፪ ሐሰተኞች መሲሖች ይነሣሉና ።
ወሐሳውያን ነቢያት ።
የነቢያትም ሐሰተኞች ።
እስመ ይገብሩ ተአምረ ወመንክረ ከመ ያስሕቱ ።
ያስቱ ዘንድ ምልክትና ተአምራት ያደርጋሉ ።
ወሶበሂ ይትከሀሎሙ ለኅሩያኒሆሂ እምአስሐትዎሙ
ቢቻላቸውም የተመረጡትንም ባሳቷቸው ነበር ።

፳፫ ወአንትሙሰ ዑቁ ።
፳፫ እናንተ ግን ዕወቁ ።
ናሁ አቅደምኩ ወነገርኩክሙ ኵሎ ።
እነሆ አስቀድሞ ነገርኋችሁ ።

በእንተ ምጽዋቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው

፳፬ ወባሕቱ ይእተ አሚረ ምስለ ኵሉ ሕማም ፀሐይኒ ይጸልም ኢሳ፡ ፲፫ ፡ ፲ ሕዝ፡ ፴፪፡ ፯ ኢዩኤ፡ ፪፡ ፲
፳፬ ነገር ግን በዚያ ወራት ከዚህ ሁሉ መከራ ጋራ ፀሐይ ትጨልማለች ።
ወወርኅኒ ኢይሁብ ብርሃኖ ።
ጨረቃም ብርሃኑንም አይሰጥም ።

፳፭ ወከዋክብትኒ ይወድቁ እምሰማይ ።
፳፭ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ ።
ይትከወስ ኃይለ ሰማያት ።

የሰማያት ኃይልም ይናወጣል ።
፳፮ ወአሜሃ ይሬእይዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዘ ይመጽእ በደመና ምስለ ኃይል ወብዙኅ ስብሐት ።
፳፮ ያን ጊዜ ከብዙ ምስጋናና ከኃይል ጋራ በደመና ሲመጣ የሰው ልጅ ክርስቶስን ያዩታል ።
፳፯ ወይእተ አሚረ ይፌንዎሙ ለመላእክቲሁ ማቴ፡ ፳፬ ፡ ፴፩ ።
፳፯ ያን ጊዜም መላእክትን ይሰዳቸዋል ።
ወያስተጋብእሙ ለኅሩያኒሁ እም፬ቱ ነፋሳት ።
የተመረጡትን ካራቱ ነፋሳት ይሰበስቧቸዋል ።
ወእምአጽናፈ ምድር እስከ አጽናፈ ሰማይ ፡
ከምድር ዳር እስከ ሰማይ ዳርቻ ።
፳፰ ወእምበለስ እእምሩ እምሳሊሁ ።
፳፰ ምሳሌውንም በበለስ ዕወቁ ።
ወእምከመ ኮነ ዐጽቃ ድኩመ ጫፏ የለመለመ ።
ወሠረጸ ቈጽላ ።
ቅጠሏም የለመለመ እንደሆነ ይትዓወቅ ከመ እል ጸቀ ማዕረር ።
መከር እንደደረሰ ይታወቃል ።
፳፱ ወከማሁ አንትሙኒ እምከመ ርኢክሙ ዘንተ ኵሎ ከመ ኮነ ።
፳፱ እንደዚህም እናንተም ይህን ሁሉ እንደ ተደረገ ያያችሁ እንደሆነ ።
እእምሩ ከመ በጽሐ ኀበ ኆኅት ።
ወደደጅ እንደደረሰ ዕወቁ ።
፴ አማን እብለክሙ ከመ ኢተኃልፍ ዛቲ ትውልድ ዘእንበለ ይኩን ዝንቱ ኵሉ ።
፴ ይህ ሁሉ ሳይሆን ይህች ትውልድ አታልፍም ብዩ እንዳታልፍ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፴፩ ሰማይ ወምድር የኃልፍ ።

፴፩ ሰማይና ምድር ያልፋል ።
ወቃልየሰ ኢየኃልፍ ።
ቃሌ ግን አያልፍም ።

፴፪ ወበእንተሰ ይእቲ ዕለት ወይእቲ ሰዓት አልቦ ዘየአምራ ።

፴፪ ያችን ቀን ግን ያችንም ሰዓት የሚያውቃት የለም ።
ወኢመላእክተ ሰማይ ።
በሰማይ የሚኖሩ መላእክትም ።
ወኢወልድ ፤ ልጅም ።
ዘእንበለ አብ ባሕቲቱ ።
ከአብ ብቻ በቀር ።
ዑቁ ፤ ተጠበቁ ።

፴፫ ትግሁ ወጸልዩ ። ማቴ፡ ፳፬ ፡ ፵፪ ።
፴፫ ተግታችሁ ጸልዩም ።
እስመ ኢተአምሩ ማዕዜ መዋዕለ ጊዜሁ ።
የጊዜውን ወራት መቼ እንደሆነ አታውቁምና ።

፴፬ እስመ ከመ ብእሲ ዘይነግድ ወየኃድግ ቤቶ
፴፬ ቤቱን ትቶ እንደሚሄድ ሰው ነውና ።
ወይሁቦሙ ግብሮ ለአግብርቲሁ ለለ፩ዱ እምኔሆሙ።
ከባሮቹ ላንዱም ላንዱ ሥራቸውን እንደሚሰጣቸው።
ወይኤዝዞ ለአጻዊኒ ከመ ይትጋህ ።
በረኛውንም እንዲተጋ ያዘዋል ይተጋ ዘንድ አእምሮውን ያዘዋል ።

፴፭ ትግሁ እንከ ፤
፴፭ እንግዲህ ትጉ ።
እስመ ኢተአምሩ ማዕዜ ይመጽእ በዓለ ቤት ።
ባለቤት መቼ እንዲመጣ አታውቁምና ።
አመሂ ሠርከ ።
በሠርክም እንደሆነ ።
ወእመሂ መንፈቀ ሌሊት ።
በሾለ ሌሊትም እንደሆነ ።
ወእመሂ ጊዜ ይነቁ ዶሮሆ ።
ዶሮ ሲጮህም እንደሆነ ።
ወእመሂ ጸቢሐ ።
ማለዳም እንደ ሆነ ፤ ሐተታ ጠርዝና ጠርዙን ይዞ ተናገረ ።

፴፮ ኢይምጻእከሙ ግብተ ወኢይርከብከሙ እንዘ ትነውሙ ።

፴፮ ድንገት እንዳይመጣባችሁ ተኝታችሁም እንዳያገኛችሁ ።

፴፯ ወናሁ እብለከሙ ለኵልክሙ ትግሁ ።
፴፯ እነሆ ለሁላችሁም ትጉብየ እነግራችኋለሁ

ዘከመ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት
ይቅትልዎ ለኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፲፬

፩ ወእስከ ሰኑይ መዋዕል ይከውን ፋሲካ በዓለ ናዕት ። ማቴ፡፳፮ ፡ ፪ ሉቃ ፳፪ ፡ ፩ ።

፩ እስከ ሁለት ቀን ፋሲካ በዓለ ናዕትም ይሆናል ።
ወየኀሥሡ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ይትአየኑዎ ወየአኃዝዎ ወይቅትልዎ ።
የካህናት አለቆችና ጻፎች ተተንኩለው ይዘው ሊገሉት ይሹ ጀመር ።

፪ ወይቤሉ አኮ በበዓል ከመ ኢይትሀወኩ ሕዝብ ።

፪ ሕዝቡ እንዳይታወኩ ግን በበዓል አይደለም አሉ ።

በእንተ ዘከመ ረፈቀ በቢታንያ ለምሳሕ
፫ ወእንዘ ሀሎ ቢታንያ በቤተ ስምዖን ዘለምጽ እንዘ ይረፍቅ ። ማቴ፡፳፮ ፡ ፮ ዮሐ ፲፪ ፩ ።
፫ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ተቀምጦ ሳለ ።
መጽአት ብእሲት ።
ሴት መጣች ።
ወእምጽአት ዕፍረተ ዘአልባስጥሮስ ዘናርዱ ።
የጣፈጠ ናርዶስ የሚባል ሽቱ አመጣች ።
ቅድው ፤ ያማረ ።
ዘዕጹብ ሤጡ ፤
ዋጋው ብዙ የሆነ ። ሐተታ ማቴዎስ ዘቢረሌ ይላል ማርቆስ ዘናርዱ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም የሁለት ቀን ትምህርት የልሳን መለያየት ነው ፤ አንድም ጭቃው የቢረሌ ነውና ማቴዎስ ዘቢረሌ አለ ሥራው የናርድ ነውና ማርቆስ ዘናርዱ አለ፤አንድም ጭቃውም ሥራውም የብርሌ ነው ናርዱ የሽቱ ስም ነው ።
ወአኮሰቶ ፤
ነቀነቀችው ፤ ቀላቀለችው አዋሐደችው ።
ወሶጠት ዲበ ርእሱ ፤
በራሱ ላይ አፈሰሰችው ፤
ወቦ እለ ተምዑ ፤
የተቆጡም ሰዎች ነበሩ ።

፬ ወይቤሉ ለምንት ዘመጠነዝ ኃጕል ዘዝ ዕፍረት ።

፬ የዚህ ሽቱ ይህን ያህል ጥፋት ለምንድን ነው አሉ ።

፭ እምኢተክህለኑ ይሠየጥ ዝንቱ ዕፍረት ፈድፋደ እም፫፻ት ዲናር ወይትወሀብ ለነዳያን ።

፭ ይህ ሽቱ ከሦስት መቶ ወቄት በሚበዛ ተሽጦ ለድሆች ይሰጥ ዘንድ ባልተቻለም ነበር አሉ ።
ወገሠጽዋ ፤ ገሠጹዋትም ።

፮ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኅድግዋ ለብእሲት ወኢታሥርኅዋ ።

፮ ጌታም ተዋት አታድክሟት እለ ሠናየ ግብረ ገብረት ላዕሌየ ።
በኔ መልካም ሥራ ሠራች ።

፯ ወለነዳያንሰ ዘልፈ ትረክብዎሙ ።

፯ ድኆችንስ ዘወትር በናንተ ዘንድ ታገኙዋቸዋላችሁ ።
ወጊዜ ፈቀድክሙ ታሤንዩ ላዕሌሆሙ ።
በወደዳችሁም ጊዜ ትመጸውቷቸዋላችሁ ፤
ወኪያየሰ አኮ ዘልፈ ዘትረክቡኒ ።
እኔን ግን ዘወትር የምታገኙኝ አይደላችሁም ።

፰ ወዛቲኒ ዘባቲ ገብረት ወአቅደመት ወቀብዓተኒ አገርየ ።

፰ ይህችም አስቀድማ ያደረገችውን እገሬንም የቀባችኝን ለምቀበርበት አደረገችው ።

፱ አማን እብለክሙ ኀበ ሰበክዎ ለዛቲ ወንጌል ውስተ ኵሉ ዓለም ይነግሩ ዘገብረት ዛቲኒ ።

፱ ወንጌሉን በሚያስተምሩበት ይህች ሴት የሠራችውን ይነግሩላታል ።
ወይዜክርዋ ፤
ያስቡታል ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ።

ዘከመ ሜጠ ይሁዳ

፲ ወይሁዳ አስቆሮታዊ ፩ዱ እም፲ቱ ወ፪ቱ ሖረ ኀበ ሊቀ ካህናት ከመ ያግብኦ ሎሙ። ማቴ ፳፮፥፲፬

፲ ከሥራ ሁለቱ አንዱ የአስቆሮት ሰው የሚሆን ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጣቸው ወደ ሊቀ ካህናት ዘንድ ሄደ ።

፲፩ ወሰሚዖሙ ተፈሥሑ ።

፲፩ በሰሙም ጊዜ ደስ አላቸው ።
ወተናገርዎ የሀብዎ ፴ ብሩረ ።
ሠላሳ ብር ሊሰጡት ተነጋገሩት ።
ወፈቀደ በጽሚት ያግብኦ ሎሙ ።
በስውር አሳልፎ ሊሳጣቸውም ወደደ ።

በአንተ ደኅሪት ድራር ወአስተዳልዎት ።

፲፪ ወአመ ቀዳሚት ዕለት በዓለ መጸለት ፋሲካ አመ ይጠብሑ ፍሥሐ ። ማቴ ፳፮ ፥ ፲፯ ሉቃ ፳፪ ፥ ፯

፲፪ በጉን በሚያርዱበት ጊዜ በመጀመሪያው ፋሲካ በቂጣ በዓልም ።
ወይቤልዎ አርዳኢሁ በአይቴ ትፈቅድ ናስተዳሉ ለከ ፍሥሐ ትብላዕ ።
ደቀ መዛሙርቱ ፋሲካውን ትበላ ዘንድ በየት ብናዘጋጅልህ ትወዳለህ አሉት ።

፲፫ ወፈነወ ፪ተ እምአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ሑሩ ሀገረ ዘቅድሜክሙ ።

፲፫ ወደፊታችሁ ካለ አገር ሂዱ ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ላከ ።
ወትረክቡ ብእሴ ዘይጸውር ፃሕበ ማይ ፤
የውኃ ማድጋ የተሸከመ ሰው ታገኛላችሁ ።
ወትልውዎ ኀበ ቦአ ።
ወደገባበት ተከተሉት ።

፲፬ ወበልዎ ለበዓለ ቤት ይቤለከ ሊቅ አይቴኑ ጽርሕ ኀበ እበልዕ ፍሥሐ ምስለ አርዳእየ ።

፲፬ የዚህን ቤት ባለቤት መምህር ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ፋሲካ የምበላበት አዳራሽ ወዴት ነው ብሎሃል በሉት ።

፲፭ ወውእቱ ያርእየክሙ ጽርሐ ዓቢየ ወንጹፈ ወርቡየ ።

፲፭ እሱም የተጌጠና የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል ።
ወህየ አስተዳልዉ ለነ ፤
በዚያ አዘጋጁልን ።

፲፮ ወሖሩ አርዳኢሁ ሀገረ ። ማቴ ፳፮ ፥ ፳ ሉቃ ፳፪ ፥ ፲፬ ።

፲፮ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ከተማ ሄዱ ።
ወረከቡ በከመ ይቤሎሙ ።
እንደ ነገራቸው አገኙ ።
ወአስተዳለው በህየ ፍሥሐ ።
ፋሲካውንም በዚያ አዘጋጁ ።

፲፯ ወመስዮ ሖረ ምስለ ፲ቱ ወ፪ቱ አርዳኢሁ ።

፲፯ ሲመሽ ከሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋራ ሄደ ።

ዘከመ ከሠተ ለሐዋርያት ዘያገብኦ

፲፰ ወእንዘ ይረፍቁ ወይበልዑ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አማን እብለክሙ ፩ዱ እምኔክሙ ዘይበልዕ ምስሌየ ያገብአኒ ። ዮሐ፲፫ ፥ ፳፩ ።

፲፰ ተቀምጠው ሲበሉ ጌታ ከናንተ አንዱ ከኔ ጋራ የሚበላው ያሲዘኛል ብየ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ።

፲፱ ወአኀዙ ይቴክዙ ወየኃዝኑ ወይበሉ በበ ፩ አነኑ አንጋ ውእቱ ።

፲፱ አንዳች እኔ እሆን እያሉ ያዝኑም ጀመር ።

፳ ወአውሥአ ። መለሰ ፤

፳ ወይቤሎሙ ፩ እም ፲ ወ፪ ዘይጸብሕ ምስሌየ ውስተ መጽብሕየ ።
በገበታ እጁን ከኔ ጋራ ወደ ወጭት የሚጠልቅ ከሥራ ሁለቱ አንዱ ነው አላቸው ።

፳፩ ወልደ ዕጓለ እመሕያውስ የሐውር በከመ ጽሑፍ በእንቲአሁ ። መዝ ፵ ፥ ፱ ግብ ፩ ፥ ፲፮

፳፩ የሰው ልጅ ክርስቶስ ግን ስለሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል ።
ወባሕቱ አሌ ሎቱ ለውእቱ ብእሲ ዘእምኔሁ ይትሜጠውዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

ነገር ግን የሰው ልጅ ክርስቶስን አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ ሰው ወዮለት ።
እምኀየሶ ሶበ ኢተወልደ ለውእቱ ብእሲ ።
ለዚያ ሰው ባልተወለደ በተሻለው ነበር ።

ዘከመ ሠርዓ አኰቴተ ቍርባን

፳፪ ወእንዘ ይበልዑ ነሥአ ኅብስተ ባረከ ወፈተተ ። ማቴ ፳፮ ፣ ፳፮ ።

፳፪ ሲበሉ ኅብስቱን ይዞ ባረከ ቆረሰም ።
ወወሀቦሙ ፤ ሰጣቸው ።
ወይቤሎሙ ንሥኡ ዝውእቱ ሥጋየ ።
ይህ ሥጋየ ነው ንሡ አላቸው ።

፳፫ ወነሥአ ጽዋአ ፤

፳፫ ጽዋውንም ያዘ ።
ወአእኰተ ወወሀቦሙ ።
አመስግኖም ሰጣቸው
ወይቤሎሙ ንሥኡ
ንሡም አላቸው ።
ወሰትዩ እምኔሁ ኵልክሙ ፤
ሁላችሁም ከሱ ጠጡ ።

፳፬ ወይቤሎሙ ዝውእቱ ደምየ ዘሐዲስ ሥርዓት ዘይትከዓው በእንተ ብዙኃን ።

፳፬ ስለ ብዙ ሰዎች የሚፈስ የሐዲስ ሥርዓት ደሜ ይህ ነው ንሡ አላቸው ።

፳፭ አማን እብለከሙ ኢይሰቲ እምዝንቱ ፍሬ ወይን እስከ እንታክቲ ዕለት አመ እስትዮ ሐዲሰ በመንግሥተ እግዚአብሔር ፤

፳፭ በእግዚአብሔር መንግሥት ታድሼ እስከ ምጠጣበት እስከዚያች ቀን ድረስ ከዚህ ወይን ፍሬ አልጠጣም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

ዘከመ ኀደግዎ ሐዋርያት ለኢየሱስ ።

፳፮ ሰቢሖሙ ወእንቢቦሙ ወጽኡ ውስተ ደብረ ዘይት ፤

፳፮ አመስግነውም ወደ ደብረ ዘይት ወጡ።

፳፯ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ኵልክሙ ትክህዱኒ በዛቲ ሌሊት። ዮሐ ፲፮ ፴፪ ዘካር ፲፫ ፯ ።

፳፯ ጌታም በዚች ሌሊት ሁላችሁ ትክዱኛላችሁ አላቸው ።
እስመ ይብል መጽሐፍ እቀትሎ ለኖላዊ ወእዘርዎን ለአባግዒሁ ።
ጠባቂውን እገድለዋለሁ በጎቹንም እበትናቸዋለሁ የሚል ጽሑፍ አለና ።

፳፰ ወእምድኅረ ተንሣእኩ እቀድመክሙ ገሊላ ፤

፳፰ ከተነሣሁም በኋላ ወደገሊላ እቀድማችኋለሁ ።

፳፱ ወይቤሎ ጴጥሮስ ለእመኒ ኵሎሙ ክህዱከ አንሰ ኢይክህደከ ።

፳፱ ጴጥሮስም ሁሉ ቢክዱህ እኔ አልክድህም አለው ።

፴ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አማን እብለከ አንተ ትክህደኒ ዮም ሠልስ በዛቲ ሌሊት ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ፪ተ ጊዜ ፣

፴ ጌታም ዶሮ ሳይጮህ ሁለት ጊዜ በዚህች ሌሊት ሦስት ጊዜ ትክህደኛለህ ብየ በውነት እነግርሃለሁ ። ሐተታ ማቴዎስ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ አለ ፥ ማርቆስ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ክልኤ ጊዜ አለ ፥ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ። ዶሮው ጊዜው ሳይደርስ በተአምራት ጮኋል። ማቴዎስ የተአምራቱ ትቶ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ አለ ማርቆስ የተአምራቱን ቈጥሮ ክልኤ ጊዜ አለ ። አንድም ዶሮ መጀመሪያ ጮሆ ይዘገያል ኋላ ቀጥሎ ቀጥሎ ይጮሀል ። ማቴዎስ የመጀመሪያውን ትቶ ዶሮ ሳይጮህ አለ ። ማርቆስ የመጀመሪያውን ቈጥሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮህ አለ ።

፴፩ ወአፈድፈደ ጴጥሮስ ተኃልፎተ ወትምክህተ እንዘ ይብል እመ ወትሂ ምስሌከ ወኢይክህደከ ።

፴፩ ጴጥሮስም ካንተ ጋራ እሞታለሁ እንጂ አልክድህም ብሎ ነገር ማበርታትንና ትምክህትን አበዛ ።
ወከማሁ ይቤሉ ኵሎሙ ።
ሁሉም እንደሱ አሉ ።

ዘከመ ጸለየ በጌቴሴማን ።

፴፪ ወሖሩ ዐጸደ ወይን እንተ ስማ ጌቴሴማን ማቴ፡፳፮፡፴፮፡ሉቃ ፳፪፡ ፵ ።

፴፪ ጌቴሴማን የሚባል ወደ ወይን ቦታ ሄዱ ወይቤሎሙ ንበሩ ዝየ እስከ አሐውር ኪያ እጼሊ ፤ እጸልይ ዘንድ ወዲያ እስከሄድ ከዚያ ቆዩኝ አላቸው

፴፫ ወነሥአሙ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ

፴፫ ያዕቆብና ጴጥሮስ ዮሐንስንም ከሱ ጋራ ወሰዳቸው ።
ወአኀዘ ይደንግፅ ወይትከዝ ።
ያዝን ያቀረቅርም ጀመረ ።

፴፬ ወይቤሎሙ ተከዘት ነፍስየ እስከ ለሞት ።

፴፬ ነፍሴ እስክትሞት አዝናለችና ።
ንበሩ ዝየ።ከዚህ ቆዩ ወትግሁ እንከ።ትጉም አላቸው።

፴፭ ወእምዝ ተአተተ ሕቀ ወሰገደ ውስተ ምድር ወጸለየ ።

፴፭ ከዚህም በኋላ ጥቂት እልፍ ብሎ ከምድር ሰገደ ጸለየ ።
ከመ ትኅልፍ እምኔሁ ይእቲ ሰዓት ለእመ ይትከሃል ።
የሚቻል እንደሆነ ያች ሰዓት ከሱ ታልፍ ዘንድ ።

፴፮ ወይቤ አባ ወአቡየ ዙሉ ይትከሃለከ አኅልፍ እምኔየ ለዛቲ ጽዋዕ ።

፴፮ አባቴ ሆይ ሁሉ ይቻልሃል ይህችን ጽዋ ከኔ አሳልፋት አለው ።
ወባሕቱ ፈቃደ ዚአከ ይኩን ወአኮ ፈቃደ ዚአየ ።
ነገር ግን ያንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የኔ ፈቃድ አይደለም ።

፴፯ ወገቢአ ረከቦሙ እንዘ ይነውሙ ።
፴፯ መጥቶም ተኝተው አገኛቸው ።
ወይቤሎ ለጴጥሮስ ስምዖን ትነውምኑ ።
ጴጥሮስንም ስምዖን ሆይ ትተኛለህን አለው ።
ወኢትክልኑ ተዓግሦ አሐተ ሰዓተ ።
አንድ ሰዓት መታገሥ አይቻልህምን አለው ።

፴፰ ትግሁ ወጸልዩ ከመ ኢትባኡ ውስተ መንሱት ።

፴፰ ወደ መከራ እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም ።
እስመ መንፈስ ይፈቅድ ወሥጋ ይደክም ።
መንፈስ ይወዳልና ሥጋ ግን የደከመ ነው ።

፴፱ ወሖረ ካዕበ ወጸለየ ወከማሁ ከመ ይቤ ።
፴፱ ሁለተኛም ሂዶ ያኑ ብቻ ጸለየ ።
፵ ወገቢአ ካዕበ ረከቦሙ እንዘ ይነውሙ ።
፵ ዳግመኛም በተመለሰ ጊዜ ተኝተው አገኛቸው ።
እስመ ከብዳ አዕይንቲሆሙ ወኢየአምሩ ዘይነብቡ ።
ዓይኖቻቸው ከብደው ነበርና የሚናገሩትን አያውቁም ነበርና ።

፵፩ ወመጽአ በሣልስ ወይቤሎሙ ኑሙ እንከሰ ወአዕርፉ ምዕረ ።

፵፩ በሦስተኛውም መጥቶ እንግዲህስ ተኙ አንድ ጊዜም ዕረፉ ።
እስመ ናሁ በጽሐ ጊዜሁ ።
ጊዜው ደርሏልና ።
ወናሁ ያገብእዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ውስተ እደ ኃጥአን ።
እነሆ የሰው ልጅ ክርስቶስ በኃጥአን እጅ ይያዛል ።
፵፪ ተንሥኡ ንሑር ናሁ በጽሐ ዘያገብአኒ ።
፵፪ እነሆ የሚያሲዘኝ ደርሷልና ተነሡ እንሂድ አላቸው ።

ዘከመ አግብአ ይሁዳ ለኢየሱስ ወዘከመ አኀዝዎ ።

፵፫ ወእንዘ ይትናገሮሙ በጽሐ ይሁዳ አስቆሮታዊ ፩ዱ እም፲ቱ ወ፪ቱ ። ማቴ ፳፮ ፥ ፵፯ ሉቃ ፳፪ ፵፯ ዮሐ ፲፰ ፫ ።

፵፫ ሲነጋገራቸውም ካሥራ ሁለቱ አንዱ የአስቆሮት ሰው የሚሆን ይሁዳ ደረሰ ።
ወምስሌሁ ብዙኃን ሰብእ ምስለ መጣብሕ ወአብትር እምኀበ ሊቃነ ካህናት ወረበናት ወጸሐፍት ።
ብዙ ሰዎችም ከሱ ጋራ ሾተል ጐመድ ይዘው ከሸማግሎችና ከጸፎች ከካህናት አለቆችም መጡ ።

፵፬ ወወሀቦሙ ትእምርተ ዘያገብእ ።
፵፬ የሚያሲዘውም ምልክት ሰጣቸው ።
ወይቤሎሙ ዘሰዓምክዎ ውእቱ አኃዝዎ ወአጽንዕዎ ወሰድዎ ።
የምስመው እሱ ነውና አጽንታችሁ ይዛችሁ ውሰዱት አላቸው ።

፵፭ ወሶቤሃ መጽአ ኀቤሁ ወይቤሎ ረቢ ወሰዐሞ
፵፭ ያን ጊዜውን ወደሱ መጥቶ መምህር ሆይ ብሎ ሳመው ።

፵፮ ወሰፍሑ እደዊሆሙ ላዕሌሁ ወአኃዝዎ ።
፵፮ እጃቸውንም ዘርግተው ያዙት ።
፵፯ ወመልሐ መጥባሕቶ ፩ዱ እም እለ ምስሌሁ ይቀውሙ ።

፵፯ ከሱ ጋራ ቆመው ካሉት አንዱ ሾተሉን መዘዘ ።
ወዘበጦ ለገብረ ሊቀ ካህናት ።
የሊቀ ካህናቱንም ባሪያ መታው ።
ወመተረ እዝኖ ።
ጆሮውን ቆረጠው ።

፵፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ዘሠራቂኑ ትዴግኑኒ ወጻእክሙ ምስለ መጣብሕ ወአብትር ተአኀዙኒ ።

፵፰ እንደሌባ ልትይዙኝ ብትርና ሰይፍ ይዛችሁ ወጣችሁን አላቸው ።

፵፱ ወትረ እሜሪ ሀሎኩ ምስሌክሙ እሜህር በምኵራብ ።
ዘወትር በምኵራብ ሳስተምር ከናንተ ጋራ አልነበርኩምን ።
ወኢአኀዝክሙኒ ።
አልያዛችሁኝም ።
ወባሕቱ ከመ ይብጻሕ ዘውስተ መጻሕፍት ።
ነገር ግን በመጻሕፍት የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ ነው ።
፶ ወኃደግዎ ኵሎሙ አርዳኢሁ ።
፶ ወጐዩ ። ማቴ ፳፮ ፥ ፶፮ ።
ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጥለውት ሸሹ ።
፶፩ ወተለዎ ፩ዱ ወሬዛ ዘይትአጸፍ ሰንዱነ ዕራቆ ።
፶፩ ዕርቃኑን በበፍታ የሰወረ አንድ ጐበዝ ተከተለው ።
ሐተታ፡ራሱን አርቆ ፤ አንድም ቅራፍ በፍታ የለበስ ።
ወአኃዝዎ ወራዙት ።
ጐልማሶች ያዙት ።
፶፪ ወኃደገ ሰንዱኖ ወጐየ ዕራቆ ።
፶፪ በፍታውንም ጥሎ ሸሸ ።

ዘከመ ቆመ ኢየሱስ በዓውድ

፶፫ ወወሰድዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ኀበ ሊቀ ካህናት ወጸሐፍት ወረበናት ። ማቴ ፳፮ ፥ ፶፯ ሉቃ ፳፪ ፥ ፶፬ ዮሐ ፲፰ ፥ ፲፫ ።

፶፫ ጌታንም ወደ ካህናት አለቃና ወደ ጸሐፎች አመጡት ።

፶፬ ወተለዎ ጴጥሮስ እምርኁቅ እስከ ውሳጤ ሊቀ ካህናት ወነበረ ምስለ ወዓልያኒሆሙ ይስኅን መንገለ በርህ ።

፶፬ ከብላቴኖቻቸው ጋራ የሳቱ ጸዳልወደ ወደ ቀበት በኩል ተቀምጦ እሳት ይሞቅ ነበር ።

፶፭ ወኃሠሡ ሊቃነ ካህናት ወኵሉ ዓውድ ስማዕተ ሐሰት ያስተዋድይዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ከመ ይቅትልዎ ። ማቴ ፳፮ ፡ ፶፱ ።

፶፭ ሊቃነ ካህናት ሸንጎውም ጌታን ይገሉት ዘንድ ሊያካስሱት ይሹት ጀመር ።
ወኃጥኡ ፤
ነውር አጡበት ።
፶፮ ወብዙኃን እለ አስተዋደይዎ ።
፶፮ ያሳጡት ብዙ ናቸው ።
ወኢኃብረ ቃሎሙ ።
ነገራቸው ግን አንድ አልሆነም ።
፶፯ ወቦ እለ ተንሥኡ ስማዕተ ሐሰት ወነበቡ ።
፶፯ በሐሰት ተነሥተው የመስክሩም የሐሰት ምስክሮችም አሉ ።
፶፰ ወይቤሉ ንሕነ ሰማዕናሁ እንዘ ይብል አነ እነሥቶ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ዘእድ ገብሮ ወበሠሉስ አሐንጽ ካልዖ ዘእድ ኢገብሮ ። ዮሐ ፪ ፣ ፲፱ ።
፶፰ ይህን እጅ የሠራውን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስተኛው ቀን ሌላ እጅ ያልሠራው ሔሠራለሁ ሲል እኛ ሰምተነዋል አሉ ።
፶፱ ወምስለ ዝኒ ኢኃብረ ስምዖሙ ።
፶፱ ከዚህም ጋራ ምስክርነታቸው አንድ አል ሆነም ዘእድ ገብሮ ዘእድ ኢገብሮ በማለት ተለያይ ተዋል ።
፷ ወተንሥአ ሊቀ ካህናት ወሐተቶ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
፷ ሊቀ ካህናቱም ቆሞ ጌታን ጠየቀው ።
ወይቤሎ አልቦኑ ዘትሠጠው እንዘ መጠነዝ ያስተ ዋድዩከ ።
ይህን ያህል ሲያሳጡህ የምትመልሰው የለህምን አለው ።
፷፩ ወአርመመ ።   ዝም አለ ።

ወኢተሠጥዎ ፡ ወኢምንተኒ ፤
ምንም ምን አልመለሰለትም ።
ወካዕበ ሐተቶ ሊቀ ካህናት ሁለተኛም ሊቀ ካህናቱ ጠየቀው ።
ወይቤሎ አንተኑ ውእቱ ክርስቶስ ወልዱ ለቡሩክ ።
የተባረከው የአብ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን አለው ።
፷፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አነ ውእቱ ። ማቴ ፳፮ ፡ ፷
፷፪ ጌታም አዎን እኔነኝ አለው ።
ወትሬእይዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዘ ይነብር በየማነ ኃይል ።
የሰው ልጅ ክርስቶስን በኃይል ቀኝ ተቀምጦ ታዩ ታላችሁ ።
ወይመጽእ በደመና ሰማይ ።
በሰማይ ደመናም ይመጣል ።

፷፫ ወሰጠጠ አልባሲሁ ሊቀ ካህናት ።
፷፫ ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደ ።
ወይቤ ምንተ እንከ ትፈቅዱ ሎቱ ስማዕተ ።
ምን ምስክር ትሹስታላችሁ ።

፷፬ ወናሁ ለሊክሙ ሰማዕክሙ ጽርፈቶ ።
፷፬ እነሆ እናንተ ስድቡን ሰምታችሁታል ።
ምንተ እንከ ትብሉ ።
እንግዲህ ምን ትላላችሁ ።
ወአግብኡ ፍትሐ ኵሎሙ
ሁሉም ፈረዱበት ።
ወይቤሉ ይቅትልዎ ።
ሞት ይገባዋልም አሉ ።
፷፭ ወአኀዙ እምውስቴቶሙ ይውርቅዎ ።
፷፭ ከሳቸውም ወገን ይተፉበትም ጀመር ።
ወጸፍዕዎ ገጾ ፤   ፊቱንም ይጸፉት ።
ወይኰርዕዎ ርእሶ ፤
ራሱንም ይመቱት ጀመር ።
ወይቤልዎ ተነበይ ለነ ክርስቶስ መኑ ውእቱ ዘጸ ፍዓከ ።
ክርስቶስ ሆይ የመታህ ማነው ይሉት ጀመረ ።
ወኮኑ ወዓልት ይጸፍዕዎ በሕቁሎሳሊቶም መላልሰው በጥፊ መቱት ።

በእንተ ክህደተ ጴጥሮስ ።

፷፮ ወእንዘ ሀሎ ጴጥሮስ ታሕተ ውስተ ውሣጤ ዓፀድ ። ማቴ ፳፮ ፡ ፷፱ ሉቃ ፳፪ ፡ ፶፭ ዮሐ ፲፰ ፡ ፲፯
፷፮ ጴጥሮስም በቅጥሩ ውስጥ ታች ተቀምጦ ሳለ ።
መጽአት አሐቲ ወለት እምእዕማተ ሊቃነ ካህናት ።
ከካህናቱ አለቆች ገረዶች አንዲቱ መጣች ።
፷፯ ወአርአየቶ ለጴጥሮስ ይስኅን ።
፷፯ ጴጥሮስን እሳት ሲሞቅ አየችው ።
ወነጸረት ፤   አስተዋለችውም ።
ወትቤሎ አንተሂ ምስለ ኢየሱስ ገሊላዊ ሀሎከ ።
አንተም ከገሊላዊ ከኢየሱስ ጋራ ነበርክ አለችው ።
፷፰ ወክህደ ወይቤላ ኢየአምር ወኢይጤይቅ ዘትብሊ ።
፷፰ አንቺ የምትይውን አላውቀውም አላስ ተውለውም ብሎ ካደ ።
ወወፅአ አፍአ ኀበ ጸናፌ ዓፀድ ።
ከቅጥሩም ውጪ ወደ አፍአ ወጣ ።
ወነቀወ ዶርሆ ፤   ዶሮም ጮኸ ።

፷፱ ወርእየቶ ካዕበ ካልዕት ወለት ማቴ ፳፮ ፣ ፸፩
፷፱ ዳግመኛ ሌላይቱ ገረድ አየችው ።
ወትቤሎሙ ለዕለ ይቀውሙ ሀየ ዝንቱኒ እምኔሆሙ ውእቱ ።
ከዚያ ቆመው ላሉት ይህም ከሳቸው ወገን ነው አለቻቸው ።

፸ ወክህደ ካዕበ ። ሉቃ ፳፪ ፣ ፶፱ ዮሐ ፲፰ ፣ ፳፭ ።

፸ ሁለተኛ ካደ ።
ወእምድኅረ ሕቀ ካዕበ ይቤልዎ ለጴጥሮስ እለ ይቀውሙ አማን እምኔሆሙ አንተ ።
ጥቂትም ቆይቶ ቆመው ያሉት ሁለተኛ ጴጥሮስን አንተም በእውነት ከሳቸው ወገን ነህ አሉት ።
ወገሊላዊ አንተ ፤ የገሊላም ሰው ነህ ።
ወቃልከ የዓውቀከ ፤
ነገርህም ያስታውቃል ።

፸፩ ወአኀዘ ይትረገም ወይምሀል ።
፸፩ ይምል ይረገምም ጀመር ።
ከመ ኢየአምሮ ለውእቱ ብእሲ ዘትብሉ ።
ያን የምትሉትን ሰው እንዳላውቀው ብሎ ።

፸፪ ወሶቤሃ ነቀወ ካዕበ ዶርሆ ። ማቴ ፳፮ ፣ ፸፭ ዮሐ ፲፰ ፣ ፳፯ ።

፸፪ ያን ጊዜም ዶሮ ሁለተኛ ጮኸ ።
ወተዘከረ ጴጥሮስ ቃሎ ለእግዚእ ኢየሱስ ዘይቤሎ ሥልሰ ትክሕደኒ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ፪ኤ ጊዜ ወበከየ ።
ጴጥሮስም ጌታ ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለውን ቃል አስቦ አለቀሰ ። ማቴዎስ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ይላል ፣ ማርቆስ ሁለት ጊዜ አለ እንደምነው አይለያይም ቢሉ አይለያይም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው አልጮኸም ፣ ማርቆስ ግን ሁለት አለ ማለቱ ማታ በተአምራት ያልጊዜው ጮሆ ነበርና ሁለተኛ ሳይጮህ ሲል ነው ። አንድም ዶሮ መጀመሪያአንድጊዜ ጮሆ ይዘገያል ኋላ ተጥሎ ተጥሎ ይጮሃል ፤ ማቴዎስ የመጀመሪያውን ትቶ ዶሮ ሳይጮህ አለ ፤ ማርቆስ የመጀመሪያውን ቈጥሮ ሁለተኛ ሲጮህ አለ ።

ዘከመ አቀምዎ ለኢየሱስ ቅድመ ጲላጦስ ።

ምዕራፍ ፲፭

፩ ወሶበ ጸብሐ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት ወረበናት ወጸሐፍተ ሕዝብ ወኵሉ ዓውድ ። ማቴ ፳፯ ፣ ፩ ። ሉቃ ፳፪ ፣ ፷፮ ዮሐ ፲፰ ፣ ፳፰ ።

፩ በነጋም ጊዜ ሸማግሎችና የካህናት አለቆች የሕዝቡም ጸፎች ሸንጎውም ሁሉ ተማከሩ ።
ወሐመድዎ ለኢየሱስ ።
ኢየሱስንም አሠሩት ።
ወወሰድዎ ወመጠውዎ ለጲላጦስ ።
ወስደውም ለጲላጦስ ሰጡት ።

፪ ወተስእሎ ለጲላጦስ ።
፪ ጲላጦስም ጠየቀው ።
ወይቤሎ አንተኑ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።
የአይሁድ ንጉሣቸው አንተን ነህ አለው ።

፪ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ። ማቴ ፳፯ ፣ ፲፩ ። ሉቃ ፳፫ ፣ ፪ ዮሐ ፲፰ ፣ ፴፫ ።

፪ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ አንተ ትብል ።
አንተ ትላለህ አለው ።
ወአስተዋደይዎ ሊቃነ ካህናት ብዙኀ ።
የካህናት አለቆችም ብዙ አሳጡት ።
ወውእቱሰ አልቦ ዘአውሥአ ።
እሱ ግን ምንም ምን የመለሰው የለም ።

፬ ወሐተቶ ካዕበ ጲላጦስ ።
፬ ጲላጦስም ሁለተኛ መረመረው ።
ወይቤሎ አልቦኑ ዘትስጠው እንዘ መጠነዝ ያስተዋድዩከ ።
ይህን ያህል ሲያሳጡህ የምትመልሰው የለህምን አለው ።

፭ ወኢተሰጥዎ እግዚእ ኢየሱስ ወኢምንተኒ
፭ ጌታ ግን ምንም ምን አልመለሰለትም ።
እስከ አንከሮ ጲላጦስ ።
ጲላጦስ እስኪያደንቀው ድረስ ።
ዘከመ አስተቀደሙ ለኢየሱስ እምነ በርባን ።

፮ ወለለበዓል የሐዩ ሎሙ አሐደ እምነ ሙቁሐን ዘአብደሩ ።
፮ በበዓል በበዓል ከእስሮች የወደዱትን አንድ አንድ ያድንላቸው ነበር ።

፯ ወሀሎ ፩ዱ ዘስሙ በርባን ሙቁሕ ምስለ እለ ሐከኩ ወምስለ ቀተልተ ነፍስ ።
፯ ከነፍስ ገዳዮችና ከሸፍቶች ጋራ የታሰረ በርባን የሚሉት አንድ ሰው ነበር ።

፰ ወጸርሑ ሕዝብ ወከልሑ ወሰአሉ ይግበር በከመ ያለምድ ።
፰ እንዳለመደ ያደርግላቸው ዘንድ ጮኸው አስምተው ለመኑ ።

፱ ወአውሥአ ጲላጦስ ።
፱ ጲላጦስም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ትፈቅዱኑ አሕይዎ ሰከሙ ለንጉሠ አይሁድ ።
የአይሁድን ንጉሥ ላድንላችሁ ትወዳላችሁን አላቸው ።

፲ እስመ የአምሮሙ ከመ በቅንዓቶሙ አግብእዎ ሊቃነ ካህናት ።
የካህናት አለቆች በቅናታቸው አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቃልና ።

፲፩ ወሊቃነ ካህናትሰ ሆከምዎሙ ለሕዝብ ከመ በርባንሃ ይስአሉ ያሕዩ ሎሙ ።

፲፩ የካህናት አለቆች ግን በርባንን ያድንላቸው ዘንድ እንዲለምኑ ሕዝቡን አነሣሷቸው ።

፲፪ ወካዕበ አውሥአ ጲላጦስ ። ማቴ ፳፯ ፥ ፳፪ ሉቃ ፳፫ ፥ ፲፰ ።

፲፪ ጲላጦስም ሁለተኛ ተናገረ ።
ወይቤሎሙ ምንተ እንከ ትፈቅዱ እረስዮ ለዘተብህሉ ንጉሠ አይሁድ ።
የአይሁድ ንጉሥ የተባለውን ምን ላድርገው ትወዳላችሁ አላቸው ።

፲፫ ወካዕበ ከልሑ ወይቤሉ ስቅሎ ።
፲፫ ዳግመኛም ስቀለው ብለው ጮሁ ።
፲፬ ወይቤሎሙ ጲላጦስ ምንተ እኩየ ገብረ ።

፲፬ ጲላጦስም ምን ክፉ ሥራ ሠራ አላቸው ።
ወፈድፋደ ጸርሑ ወይቤሉ ስቅሎ ።
ስቀለው ብለው አብዝተው ጮሁ ።

፲፭ ወመከረ ጲላጦስ ይግበር ፈቃዶሙ ለሕዝብ ።

፲፭ ጲላጦስም የሕዝቡን ፈቃድ ሊያደርግ ወደደ ።
ወአሕየወ ሎሙ በርባንሃ ።
በርባንንም አዳነላቸው ።
ወቀሠፎ ለእግዚእ ኢየሱስ ወወሀቦሙ ይስቅልዎ ።
ጌታንም ገርፎ ሊሰቅሉት ሰጣቸው ።

ዘከመ ተሣለቁ ላዕለ ኢየሱስ

፲፮ ወአብእዎ ሐራ ውሳጤ ዐጸድ ኀበ ምኵናን ። ማቴ ፳፯ ፥ ፳፯ ዮሐ ፲፱ ፥ ፪ ።

፲፮ ጭፍሮች ወደ ፍርድ ዐደባባይ አገቡት ።
ወጸውዑ ኵሎ ሠገራተ ሰኢራ
ሰኢራ የሚባለውን ጭፍራ ጠሩ ።

፲፯ ወአልበስዎ ሜላተ ።
፲፯ ነጭ ሐርም አለበሱት ።
ወጸፈሩ አክሊለ ዘሦክ ወአስተቀጸልዎ ።
የሾህ አክሊል ታተው ደፉለት ።
ወይሳለቅዎ ፤ ዘበቱበት ።

፲፰ ወይቤልዎ በሐ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።
፲፰ የአይሁድ ንጉሣቸው ሆይ ደህንነት ላንተ ይሁን አሉት ።
፲፱ ወይኰርዕዎ ርእሶ በህለት ።
፲፱ ራሱንም በዘንግ መቱት ይመቱት ነበር ።
ወይወርቅዎ ፤ ይተፉበትም ነበር ።
ወያስተበርኩ ወይሰግዱ ሎቱ ።
ተንበርክከውም ይሰግዱለት ነበር ።

ዘከመ አጾርዎ መስቀሎ

፳ ወሶበ ተሣለቁ ላዕሌሁ ሰለብዎ ውእተ ሜላተ ወአልበስዎ አልባሲሁ ።

፳ ከዘበቱበትም በኋላ ያን ነጭ ሐር ገፈው ልብሱን አለበሱት ።
ወወሰድዎ ኀበ ይሰቅልዎ ።
ወደሚሰቅሉትም ቦታ ወሰዱት ።

፳፩ ወአበጡ ፩ደ ኃላፌ ፍኖት ስምዖንሃ ቀሬናዌ እትወቶ እምሐቅል ። ማቴ ፳፯ ፥ ፴፪ ። ሉቃ ፳፫ ፥ ፳፮ ።

፳፩ ከዱር ሲገባ ከመንገደኞች አንዱን ከቀሬንዮ ሰው ስምዖንን ጐተቱት ።
ወውእቱ አቡሆሙ ለእለ እስክንድሮስ ወሮፎስ ።
እሱም የሮፎስና የእስክንድሮስ አባት ነው ።
ከመ ይጹር መስቀሎ ።
መስቀሉን ሊሸከም ።

፳፪ ወወሰድዎ ብሔረ ጎልጎታ ዘበትርጓሜሁ ይብልዎ መካነ ቀራንዮ ።

፳፪ በትርጓሜው የራስ ቅል ቦታ ወደሚሉት ወደ ጎልጎታ ወሰዱት ።

፳፫ ወወሀብዎ ይስተይ ወይነ ምስለ ከርቤ ቱሱሕ ።

፳፫ ከከርቤ ጋራ የተቀላቀለ ወይን ይጠጣ ዘንድ ሰጡት ።
ወአበየ ሰትዮ ፤ አልጠጣም አለ ።

ዘከመ ተሰቅለ ኢየሱስ

፳፬ ወሰቀልዎ
፳፬ ሰቀሉትም ።
ወተአፀው ዲበ አልባሲሁ ።
ማቴ ፳፯ ፥ ፴፭ ። ሉቃ ፳፫ ፥ ፴፬ ። ዮሐ ፲፱ ፥ ፳፫ ።
በልብሱም ዕፃ ተጣጣሉ ።
ወተካፈሉ ዘከመ ይነሥኡ ።
እንደደረሳቸውም ተካፈሉ ።

፳፭ ወ፫ቱ ሰዓት ጊዜ ይሰቅልዎ ።
፳፭ በሰቀሉት ጊዜ ፫ት ሰዓት ነበረ ።
ሐተታ ፡ ማቴዎስ ቀትር ይላል ፡ ማርቆስ ሠለስት አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ፡ ማቴዎስ በንኡስ ቀትር አለ ፡ ማርቆስ በዓቢይ ቄጥር ሠለስት አለ ፤ አንድም ሁሉም በንኡስ ቈጥረዋል ፡ የማቴዎስ አይለወጥም ፡ ማርቆስ ቀትሩን ብቻ በንኡስ ቈጥሮ ።
አንድም መስቀሉን በሠለስት አዘጋጅተዋል በቀትር ሰቅለውታል ያዘጋጁበትን ሲያይ ማርቆስ ሠለስት አለ ፤ የሰቀሉበትን ሲያይ ማቴዎስ ቀትር አለ ።

፳፮ ወይብል መጽሐፈ ጌጋዩ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።

፳፮ የበደሉም ደብዳቤ የአይሁድ ንጉሣቸው ነው ይላል ።

፳፯ ወሰቀሉ ምስሌሁ ፪ተ ፈያተ ።
፳፯ ከሱም ጋራ ሁለት ወንበዶች ሰቀሉ ።
፩ደ በየማኑ ወ፩ደ በጸጋሙ ።
እንዱን በቀኙ እንዱንም በግራው ።

፳፰ ወተፈጸመ መጽሐፍ ዘይቤ ተኈለቈ ምስለ ገበርተ ዓመፃ ። ኢሳ ፶፫ ፣ ፲፪ ።

፳፰ መጽሐፍ ዓመፅን ከሚሠሩ ጋራ ተቈጠረ ያለው ተፈጸመ ።

፳፱ ኃለፍትኒ ይፀርፉ ላዕሌሁ ወየሐውሱ ርእሶሙ ። ዮሐ. ፪ ፣ ፲፱ ።
፳፱ የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበረ ። [illegible] [illegible] ለቤተ መቅደስ [illegible] [illegible] መቅደስን አፍርሰህ በሦስተኛው ቀን የምትሠራው ሆይ ፤
፴ አድህን ርእሰከ ።
፴ ራስህን አድን ።
ወረድ እመስቀልከ ።
[illegible] ውረድ አሉት ።
፴፩ ወከማሁ ሊቃነ ካህናትኒ ወጸሐፍት ይሣ[illegible] ።
፴፩ የካህናት አለቆችና ጸፎችም እንዲሁ ይዘብቱበት ነበረ ። ወይቤልዎ ዘባዕደ ያድኅን ወርእሶ ኢይክል አድኅኖ ።
ሌላውን የሚያድን ራሱን ግዳን አይቻለውም አሉ ፤
፴፪ እመሰ ውእቱ ክርስቶስ ንጉሠ እሥራኤል ለይረድኬ ይእዜ እምነ መስቀሉ ።
፴፪ የእሥራኤል ንጉሥ ክርስቶስማ ከሆነ ዛሬ ከመስቀሉ ይውረድ ፤
ወንርአይ ወንእመን ቦቱ ።
እይተንም እንመንበት ፤
ወእለሂ ተሰቅሉ ምስሌሁ ይዘነጕግዎ ፤
ተሱም ጋራ የተሰቀሉት ይላገዱት ነበረ ።

በእንተ ጻዕሩ ወሞቱ ለኢየሱስ

፴፫ ወሶበ ኮነ ጊዜ ቀትር ጽልመ ፀሐይ ፤
፴፫ ቀትር በሆነም ጊዜ ፀሐይ ጨለመ ፤
[illegible] ዓለም ጽልመ እስከ ተሱዓት ሰዓት ፤
ዓለም ሁሉም እስከ ተሳት ጨለመ ።
፴፬ ወጊዜ ተሱዓት ሰዓት ገዓረ ኢየሱስ በቃል ዐቢይ ወይቤ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ መዝ·፳፩፡፩ ማቴ· ፳፯ ፣ ፵፮ ።
፴፬ በተሳትም ኢየሱስ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ቃል ጮኸ ።
[illegible] አምላኪየ አምላኪየ ለምንት ተኃድገኒ ።
በትርጓሜውም አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ ማለት የሚሆን ።

፴፭ ወቦ እለ ይቤሉ እምእለ ይቀውሙ ህየ ኤልያስሃ ይጼውዕ ።

፴፭ ከዚያ ቁመው ካሉትም ኤልያስን ይጠራል ያሉ አሉ ።

፴፮ ወሮፀ ፩ዱ ።
፴፮ አንዱም ሮጠ ።
ወመልአ ሰፍነገ ብሒዓ ።
መጣጣውንም በሰፍነግ መላ ።
ወአሰረ በህለት ። በዘንግም አሰረው
ወአስተዮ ። አጠጣውም ።
ወይቤ ኅድጉ ንርአይ ለእመ ይመጽእ ኤልያስ ያወርዶ ።
ኤልያስ ሊያወርደው ይመጣ እንደሆን ተው እንይ አለ
፴፯ ወገዓረ ኢየሱስ በዓቢይ ቃል
፴፯ ኢየሱስ ግን በታላቅ ቃል ጮኸ ።
ወመጠወ ነፍሶ ።
ነፍሱንም ሰጠ ።
፴፰ ወተሠጠ መንጦላዕተ ምኵራብ ለ፪ኤ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ ።
፴፰ የመቅደሱም መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ ።
፴፱ ወርእዮ ሊቀ ፻ ዘይቀውም መንጸረ ከመ ከመዝ ገዓሮ ሞተ ።
፴፱ በአንጻር ቁሞ የነበረው የመቶውም አለቃ እንዲህ ጮሆ እንደሞተ ባየ ጊዜ ።
ይቤ ዝንቱ ብእሲ አማን ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ
ይህ ሰው በውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነው አለ ።
፵ ወሀለዋ አንስት ይቀውማ ወይኔጽራ እምርኁቅ ። ማቴ· ፳፯ ፣ ፶፭ ።
፵ ሴቶችም ርቀው ቁመው ያዩ ነበረ ።
፵፩ ወማርያም መግደላዊት ወማርያም እመ ያዕቆብ ዘይንእስ ሉቃ ፣ ፰ ፣ ፪ ፤
፵፩ እኒህም የታናሹ ያዕቆብ እናት ማርያምና ማርያም መግደላዊት ናቸው ።
ወእሙ ለዮሳ ወሰሎሜ እለተለዋሁ እምገሊላ ወተልእካሁ ተገሊላ ጀምረው የተከተሉትና ያገለገሉት ሰሎሜና የዮሳም እናት ናቸው ።
ወባዕዳትሂ ብዙኃት እለ ዓርጋ ምስሌሁ ኢየሩሳሌም ከሱ ጋራ ወደኢየሩሳሌም የወጡ ሌሎችም ብዙዎች

ዘከመ ተቀብረ ኢየሱስ ።

፵፪ ወመስዮ ዓርብ እሜሃ በዕለተ ሰንበት ውእቱ ማቴ ፳፯ ፣ ፶፯ ፤ ሉቃ ፳፫ ፣ ፶ ፤ ዮሐ ፲፱ ፣ ፴፰ ።

፵፪ ዓርብ ሲመሽ ያን ጊዜም የሰንበት መግቢያ ነበር ።

፵፫ መጽአ ዮሴፍ እምአርማትያስ ብእሲ ኄር ።
፵፫ ከአርማትያስ ዮሴፍ የሚባል ደግ ሰው መጣ
ወጠቢብ ብሉሕ ነበር ።
ወውእቱ ይሴፎ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
እሱም የእግዚአብሔርን መንግሥት ተስፋ ያደርግ ነበር ።
ወተሀበለ ወቦአ ኀበ ጲላጦስ ወሰአለ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ወደ ጲላጦስም ደፍሮ ገብቶ የጌታን ሥጋ ለመነ ።

፵፬ ወአንከረ ጲላጦስ እፎ ሞተ ።
፵፬ ጲላጦስም እንዴት ሞተ ብሎ አደነቀ ።
ወጸውዖ ለሐራዊ ።
ወይቤሎ ወድዓኑ ሞተ ።
የጭፍራውንም አለቃ ጠርቶ ፈጽሞ ሞቷል አለው ።
ወይቤ እወ ሞተ ።
አዎን ሞተ አለው ።

፵፭ ወአእሚሮ በኀበ ሐራዊ ከመ ሞተ አዘዘ ይጸግዎ ለዮሴፍ ሥጋሁ ።

፵፭ እንደሞተም ከጭፍራው አለቃ በተረዳ ጊዜ ሥጋውን ለዮሴፍ ይሰጠው ዘንድ አዘዘ ሐተታ ጲላጦስ ሞተ ብሎ ጠየቀሁ ፤ እወ ሞተ ፤ አዎን ሞተ አለው ። እፎ ሞተ እንዴት ሞተ አለው ። ከመ ከመዝ ግዒሮ ሞተ ። ዓለሙን እንዲህ በታምራት አስጨንቆት አስጠብቦት ሞተ አለው መሞቱን ዐውቆ ለዮሴፍ አውርድ አለው ። አንድም ሐራዊ ሞተ ብሎ ነገረው ። ጲላጦስ ወድአኑ ሞተ ፤ ፈጽሞ ሞተን አለው ። እወ ሞተ ፤ አዎን ሞተ አለው ። ጲላጦስ እንዴት ሞተ ብሎ አድንቆ አውርድ ብሎ አሰናበተው
፵፮ ወተሣየጠ ዮሴፍ ሰንዱናተ
፵፮ በፍታም ገዛ ።
ወአውረዶ ወገነዞ በሰንዱናት ።
አውርዶም በበፍታ ገነዘው ።
ወቀበሮ ውስተ መቃብር ሐዲስ ዘአውቀረ ውስተ ኰኵሕ ባስጠረበውም ደንጊያ ውስጥ ቀበረው ።
ወአንኰርኰረ እብነ ውስተ አፈ መቃብር ።
ደንጊያውንም ከመቃብሩ አፍ ገጠመ ።
፵፯ ማርያም መግደላዊት ወማርያም እመ ዮሳ ርእያ ኀበ ቀበርዎ ።
፵፯ የዮሳ እናት ማርያምና ማርያም መግደላዊት የቀበሩበትን ቦታ ያዩ ነበር ።

በእንተ ትንሣኤሁ ለኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፲፮ ።

፩ ወሶበ ኀለፈት ሰንበት ማርያም መግደላዊት ወማርያም እመ ያዕቆብ ወሰሎሜ ተሣየጣ አፈወ ከመ ይምጽአ ወይቅብኦ ሥጋሁ ፤ ማቴ· ፳፰፥፩ ። ሉቃ· ፳፬፥፩ ። ዮሐ· ፳፥፩ ።

፩ ሰንበት ባለፈች ጊዜም የያዕቆብ እናት ማርያምና የመግደላዊቱ ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሥጋውን ይቀቡ ዘንድ ሽቱ ገዙ ።

፪ ወሐሩ ወእንግሐ ጥቀ ሐዊረ ኀበ መቃብር በእሑድ ሰንበት ።

፪ በመጀመሪያውም ሰንበት ፈጽሞ ማልደው ወደመቃብር ሄዱ ።

፫ ወሶበ ሠረቀ ፀሐይ ይቤላ በበይናቲሆሙ መኑ ይከሥታ ለነ ለእብን እምኆኅተ መቃብር ።
፫ ፀሐይ በወጣች ጊዜም ደንጊያውን ከመቃብሩ አፍ ማን ያነሣልናል አሉ ። ሐተታ ደርሰዋል ቢሉ ማን ያነሣልን አልደረሱም ቢሉ ማን ያነሣልናል አሉ ።
፬ ወረከባ ርእያሁ ለእብን ኀበ አንኰርኰረት ።
፬ ፈጥነውም ሄደው ደንጊያይቱን ተገልብጣ አዩዋት ።
ወዓባይ ይእቲ ጥቀ ፤
እጅግም ታላቅ ነበረች ።
፭ ወበዊአን ውስተ መቃብር ረከባ ፩ደ ወሬዛ እንዘ ይነብር መንገለ የማን ። ማቴ· ፳፰፥፩ ። ሉቃ· ፳፬፥፬ ። ዮሐ ፳፥፲፪ ።
፭ ወደ መቃብር በገቡም ጊዜ አንድ ጉልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩ ።
ወይለብስ አልባሰ ንጹሐ ፤
ነጭ መጎናጠፊያ ለብሶ ።
ወደንገፃ ።   ደነገጡም ።
፮ ወይቤሎን መልአክ ኢትደንግፃ ።
፮ አትደንግጡ አላቸው ።
ኢየሱስሃኑ ናዝራዊ ዘተሰቅለ ተኃሥሣ ።
የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትሻላችሁን ።
ተንሥአ ።   ተነሣ ።
ወኢሀሎ ዝየሰ ። ከዚህስ የለም ወናሁ መካኑ ኀበ ተቀብረ ። እነሆ የተቀበረበት ቦታ ፤
፯ ወባሕቱ ሑራ ንግራሆሙ ለአርዳኢሁ ወለጴጥሮስ ከመ ይቀድሞሙ ገሊላ ።
ማር· ፲፬፥፳፰ ።
፯ ወደገሊላ እንዲቀድማቸው ሂዱችሁ ለጴጥሮስና ለደቀ መዛሙርቱ ንገሯቸው ።
ወበሀየ ይሬእይዎ በከመ ይቤሎሙ ።
እንደ ነገራቸው ከዚያ ያዩታል ፤
፰ ወወፅአ እምኔ መቃብር ወጕያ ከመቃብር ወጥተው ሸሹ ፤
፰ እስመ አኀዞን ረዓድ ወድንጋፄ ፤
ድንጋፄና መንቀጥቀጥም ይዟቸው ነበርና ፤
ወኢነገራ ወኢለመኑሂ ።

[illegible] ለማን አልተናገሩም እስመ ፈርሃ ።
ፈርተዋልና ።
[illegible] ዘአዘዞ ለጴጥሮስ ወለእሊአሁ ፈጺሞን ነገረ ።
ንገሩ ብሎ ያዘዘውን ለጴጥሮስ ለወንድሞቹ ነገረው ከረጸሙ በኋላ ። አንድም ዘአዘዞሙ ለጴጥሮስ ወለ [illegible] ለወንድሞቹ ንገሩ ብሎ ያዘዛ ቸውን ነገረው ከረጸሙ በኋላ አስተርአዮሙ እግዚ [illegible] ተገ[illegible] ።
[illegible] ከተነ[illegible] በኋላ ታያቸው ።
[illegible] እስከ ዓረብ [illegible] ለመድ [illegible] ይልዉ ወንጌለ ከሐዲ [illegible] ማለት በእራሱ ግልፀን ያስተምሩ ዘንድ ላካቸው ።

[illegible] አስተርአየ ኢየሱስ ለብዙኃን ።

፱ ወተንሢኦ በጽባሕ በእሑድ ሰንበት አስተርአያ ቅድመ ለማርያም መግደላዊት እንተ እምኔሃ አውፅአ ሰብዓተ አጋንንተ ። ዮሐ· ፳ ፣ ፲፮ ።

፱ በመጀመሪያው ሰንበት ተነሥቶም ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለማርያም በመጀመሪያ ታያት ሐተታ ፤ መልክ መልካም ተወዳጅ እኅት ነበረቻት ወዲህ ወላድ ወዲህ መወደድ ያላት በዚህ ሁሉ ምቀኝነት አድሮባታል ወዲህ መውለድ ወዲህ መወደድ እያለች በዚህ ምክንያት ሰባት አጋንንት አድረውባት ነበር መንፈስ ትዕቢት መንፈስ ፅርፈት ማለት ስድብ ፣ መንፈስ ቅንዓት መንፈስ ትውዝፍት ማለት የምንዝር ጌጥ መንፈስ ዝሙት መንፈስ ሐሜት መንፈስ ሐሰት ።

፲ ወይእቲ ሖዊራ ዜነወቶሙ ለእለ ምስሌሁ ሀለዉ ቀዲሙ እንዘ ይበክዩ ወይላህዉ ።

፲ እሷም ሄዳ አስቀድሞ ከሱ ጋራ ሲያለቅሱ ለነበሩ ነገረቻቸው ።

፲፩ ወእሙንቱኒ ሶበ ሰምዑ ከመ አስተርአያ ወሕያው ውእቱ ወኢአምንዋ ።
፲፩ እሳቸውም እንደታያት ሕያውም እንደሆነ በሰሙ ጊዜ አላመኑዋትም ።
፲፪ ወእምዝ አስተርአዮሙ ለ፪ቱ እምኔሆሙ በካልዕ ራዕይ እንዘ የሐውሩ ሐቅለ ። ሉቃ·፳፬፣፲፫ ።
፲፪ ከዚህም በኋላ ከሳቸው ወገን ለሁለቱ በበረሃ ሲሄዱ ሌላ መስሎ ታያቸው ።
፲፫ ወሖሩ እሙንቱኒ ወዜነዎሙ ለቢጾሙ ።
፲፫ እሳቸውም ሄደው ለባልንጀሮቻቸው ነገሯቸው ።
[illegible]ኒ ኢአምንዎሙ
እሳቸውንም አላመኑዋቸውም ።

፲፬ ወእምድኅረዝ ካዕበ እንዘ ይረፍቁ ፲ወ፩ዱ አስተርአዮሙ
፲፬ ከዚህ በኋላ ዐሥራ አንዱ ተቀምጠው ሲበሉ ታያቸው ።
ወገሠጾሙ በእንተ ሕጸጸ አሚኖቶሙ ወጽንአ ልበሙ ስለ ሃይማኖታቸውም መጉደል ስለ ልቡናቸውም ጽናት ገሠጻቸው ። አንድም ወግዕዘ ጽንዓ ልበሙ ይላል ። የልቡናቸውን ጽናት ነቀፈ ።
እስመ ለእለ ርእይዎ ከመ ተንሥአ ኢአምንዎሙ ።
እንደ ተነሣ ያዩትን አላመኑዋቸውምና ።

ዘከመ ፈነዎሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት ።

፲፭ ወይቤሎሙ ሑሩ ወስብኩ ውስተ ኵሉ ዓለም ወስብኩ ወንጌለ ለኵሉ ፍጥረት ።

፲፭ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለሰው ሁሉ አስተምሩ አላቸው ።

፲፮ ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን ።
፲፮ ያመነም የተጠመቀም ይድናል ወዘሰ ኢአምነ ይደየን ።
ያላመነ ግን ይፈረድበታል ።
፲፯ ወዛቲ ተእምር ለእለ አምኑ በስምየ ትትል ዎሙ ። ግብ· ፲፮ ፣ ፲፰ ። ፱፥፬ ። ፲ ፣ ፵፮ ፣ ፲፰ ።
፲፯ ይህች ታምራት በስሜ ያመኑትን ትከተላ ቸዋለች ።
በስመ ዚአየ አጋንንተ ያወፅኡ ።
በኔ ስም አጋንንትን ያወጣሉ ወበካልዕ ልሳን ይትናገሩ ሐዲሳተ ።
በሌላ ቋንቋ አዲስ ነገር ይናገራሉ ።

፲፰ ወአራዊተ ምድር ይእኅዙ በእደዊሆሙ ። ሉቃ ፳፬ ፣ ፲፩ ።
፲፰ አባብ ይይዛሉ ።
ወኢይነክዮሙ ።
ጉዳት አያገኛቸውም ።
ወዘሂ ይቀትል ለእመ በልዑ ወሰትዩ አልቦ ዘየኀሥሞሙ የሚገል ነገርም ቢበሉ ቢጠጡም የሚያገኛቸው ጉዳት የለውም ።
ወዲበ ዱያን እደዊሆሙ ያነብሩ ወይሔዉኑ ።
እጃቸውን በበሽተኞች ላይ ይቃጣሉ ያኖራሉም ።
ወእሙንቱሂ ይትፌወሱ ።
እነሳቸውም ይፈወሳሉ ።

በእንተ ዕርገቱ ለኢየሱስ ።

፲፱ ወእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እምድኅረ ተናገሮሙ ዓርገ ውስተ ሰማይ ።
፲፱ ጌታ ግን ይህን ካስተማራቸው በኋላ ወደ ሰማይ ዓረገ ።
ወነበረ በየማነ አቡሁ ።
ባባቱም ቀኝ ተቀመጠ ማለት ባባቱም ዕሪና ኖረ ።

፳ ወወፂኦሙ እሙንቱ ሰበኩ በኵለሄ ።

፳ እሳቸውም ወጥተው በሥፍራው ሁሉ አስተማሩ ።

እንዘ እግዚእ ይረድእ ።
ጌታ እየረዳቸው ።
ወቃሎ ያጸንዕ በተአምር ዘይተሉ ።
ሕጉ ወንጌልንም ቀጥሎ ቀጥሎ በሚደረግ ተአምራት እያስረዳላቸው ።

መልእ ጽሒፈተ ብሥራቱ ለማርቆስ ሐዋርያ ፩ዱ እም ፸ወ ፪ቱ አርድእት ።
ከሰባ ሁለቱ አርድእት አንዱ ማርቆስ የጻፈው ወንጌል ደረሰ ተፈጸመ ።
ወኮነ ጽሒፈ በሀገረ ሮሜ በልሳነ ሮም ዘአፍርንጊ ። በሮማይስጥ ቋንቋ በሮም ሀገር የጻፈው ። ብዙ ሮም አለና ከዚያ ሲለይ ዘአፍርንጊ አለ ። ቤተ ኢየሱስ ቤተ ፈረንሲስ እንዲባል እምድኅረ ዕርገቱ ለእግዚእነ በ፲ወ፩ ዓመት ።

ጌታ ካረገ በኋላ ባሥራ አንድ ዓመት ።
ወበራብዕት ዓመተ መንግሥቱ ለቀላውዴዎስ ቄሣር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ ባራተኛው ዓመት የጻፈው ወስብሐት ለእግዚአብሔር ። አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው ።

* * *

ኍልቈ ምዕራፍ ዓቢይ ዘወንጌለ ማርቆስ ።	የማርቆስ ወንጌል ዓቢይ ምዕራፍ ቍጥር ።
ምዕራፍ ፩ ። ቀዳሚሁ ለወንጌለ ኢየሱስ ክርስቶስ	የወንጌል መጀመሪያ ።
ም ፪ ። ወቦአ ካዕበ ሀገረ ቅፍርናሆም ።	ዳግመኛ ወደቅፍርናሆም ገባ ።
ም ፫ ። ወቦአ ካዕበ ምኵራብ ።	ዳግመኛ ወደ ምኵራብ ገባ ።
ም ፬ ። ወአኀዘ ካዕበ ይምሀሮሙ ።	ዳግመኛ ያስተምር ጀመረ ።
ም ፭ ። ወበጽሑ ማዕዶተ ባሕር ኀበ ብሔረ ጌርጌሴኖን ።	ጌርጌሴኖን ባሕር ማዶ ደረሱ ።
ም ፮ ወወፂአ እምህየ ቦአ ሀገሮ ።	ከዚያ ወጥቶ አገሩን ገባ ።
ም ፯ ወተጋብኡ ኀቤሁ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን	ጸሐፍት ፈሪሳውያን ወደሱ ተሰበሰቡ ።
ም ፰ ። ወይእተ አሚረ ካዕበ ብዙኅ ሰብእ ።	በዚያ ወራት ብዙ ሰው ነበረ ።
ም ፱ ። ወእመ ሰዱስ ዕለት ነስአሙ ።	በስድስተኛው ቀን ወሰዳቸው ።
ም ፲ ። ወተንሢአ ሖረ እምህየ ።	ከዚያ ተነሥቶ ሔደ ።
ም ፲፩ ። ወአልጺቆሙ ለኢየሩሳሌም ቤተ ፋጌ	ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ።
ም ፲፪ ። ወአኀዘ ይመስል ሎሙ ።	ይመስልላቸው ጀመረ ።
ም ፲፫ ። ወወፂአ እምኵራብ ።	ከምኵራብ በወጣ ጊዜ ።
ም ፲፬ ። ወእስከ ሰኑይ መዋዕል ።	እስከ ሁለት ቀን ።
ም ፲፭ ። ወሶበ ጸብሐ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት ።	በነጋ ጊዜ የካህናት አለቆች መከሩ ።
ም ፲፮ ። ወኀለፈት ሰንበት ።	ሰንበት ካለፈች በኋላ ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ማርቆስ ።		የማርቆስ ወንጌል አርእስት ማውጫ
በእንተ ስብከተ ዮሐንስ መጥምቅ ።	ምዕራፍ ፩ ቍጥር ፩	ዮሐንስ መጥምቅ እንደ አስተማረ ።
በእንተ ጥምቀት ወተመክሮት ዘኢየሱስ ።	ቍ ፱	ስለ ጌታ መጠመቅና መፈተን ።
በእንተ ዘከመ አኀዘ ኢየሱስ ብክይስ ወይኅረይ ቀደምተ ሐዋርያት ።	ቍ ፲፬	ጌታ መጀመሪያ እንደ አስተማረና ሐዋርያትን እንደ መረጠ ።
በእንተ ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ በቅፍርናሆም ለዘቦቱ ጋኔን ።	ቍ ፳፩	ጋኔን ያደረበትን በቅፍርናሆም እንደ አዳነ ።
በእንተ ሐማተ ጴጥሮስ ወካልዓን ሕሙማን እለ ተፈወሱ ።	ቍ ፳፱	የጴጥሮስ አማትን ሌሎችም በሽተኞች እንደ ዳኑ ።
በእንተ ዘከመ ሐይወ መፃጉዕ	ም ፪ ቍ ፩	መፃጉዕ እንደ ዳነ ።
በእንተ ዘከመ ተጸውዓ ሌዊ ።	ቍ ፲፫	ሌዊ እንደ ተጠራ
በእንተ ጾም ዘክርስቲያን ።	ቍ ፲፰	ስለ ክርስቲያን መጦም ።
በእንተ ሰዊተ ሥርናይ ወሰንበት	ቍ ፳፫	ስለ ሥንዴ እሸትና ስለ ሰንበት ።
በእንተ ዘየብሰት እዴሁ ።	ም ፫ ቍ ፩	እጁ ስለ ደረቀች ሰው ።
በእንተ ካልአን ተአምራት ዘኢየሱስ ።	ቍ ፯	ጌታ ሌሎችን ታምራት እንዳደረገ ።
በእንተ ዘከመ ኅረዮሙ ለሐዋርያት ወወሀቦሙ ሥልጣነ በላዕለ አጋንንት ወድውያን ።	ቍ ፲፫	ጌታ ሐዋርያትን እንደ መረጣቸው በአጋንንትና በበሽተኞችም ላይ ሥልጣን እንደ ሰጣቸው ።
በእንተ ዘከመ አስተዋደይዎ ለኢየሱስ ከመ ያወፅአ አጋንንተ በብዔል ዜቡል	ቍ ፳፩	አጋንንትን በብዔል ዜቡል እንዲያወጣ ጌታን እንደ አካሰሱት ።
በእንተ አዝማዲሁ ለኢየሱስ	ቍ ፴፩	ስለ ጌታ ዘመዶች ።
በእንተ ምሳሌ ዘራዒ ።	ም ፬ ቍ ፩	ስለ ዘሪ ምሳሌ ።
በእንተ ዘርዕ ወማዕረር ።	ቍ ፳፮	ስለ ዘርና ስለ መከር ።
በእንተ ኅጠተ ሰናፔ ።	ቍ ፴	ስለ ሰናፍጭ ቅንጣት ።
በእንተ ኅድዓተ ማዕበል ።	ቍ ፴፭	ስለ ማዕበል ጸጥታ ።
ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ በብሔረ ጌርጌሴኖን ዘቦቱ ጥቀ አኩያን አጋንንት ።	ም ፭ ቍ ፩	ጌታ በጌርጌሴኖን ክፉዎች አጋንንት ያደሩበትን እንደ አዳነ ።
በእንተ ዘከመ ፈወሳ ኢየሱስ ለእንተ ደም ይውኅዛ ወዘከመ አንሥአ ለወለተ ኢያኢሮስ ።	ምዕራፍ ፭ ቍጥር ፳፩	ደሟ የሚፈስ ሴትን እንደ አዳነ የኢያኢሮስንም ልጅ እንደ አስነሣት ።
በእንተ ዘከመ ሰበከ ኢየሱስ በናዝሬት ።	ም ፮ ቍ ፩	ጌታ በናዝሬት እንደ አስተማረ ።
በእንተ ዘከመ ፈነዎሙ ምሂሮ ለሐዋርያት ይስብኩ ።	ቍ ፯	ሐዋርያትን አስተምሮ ያስተምሩ ዘንድ እንደሰደዳቸው ።
በእንተ ዘከመ ስምዓ ኮነ ዮሐንስ መጥምቅ ።	ቍ ፲፬	ዮሐንስ መጥምቅ እንደ መሰከረ ።
በእንተ ዘከመ ተመይጡ ሐዋርያት ።	ቍ ፴	ሐዋርያት እንደተመለሱ ።
በእንተ ዘከመ አብዝኃ በቀዳሚ ፭ተ ኅብስተ ።	ቍ ፴፬	መጀመሪያ ፭ እንጀራ እንደ አበረከተ ።
በእንተ ዘከመ ሖረ በዲበ ማይ	ቍ ፵፭	በውኃ ላይ እንደ ሔደ ።
በእንተ ዘከመ ተገብረ መንክራት በጌንሴሬጥ በገሲሰ ጽንፈ ልብሱ ።	ቍ ፶፫	በጌንሴሬጥ ልብሱን በመዳሰስ ታምራት እንደተደረገ

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ማርቆስ ።			የማርቆስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ፈሪሳውያን ወሥርዓቶሙ ።	ም ፯	ቍ ፩	ስለ ፈሪሳውያንና ስለ ሥርዓታቸውም ።
በእንተ ቀነናዊት ።		ቍ ፳፬	ስለ ቀናናዊት ።
በእንተ ዘከመ ፈወሶ ለበሐም ወጽሙም ።		ቍ ፴፩	ድዳና ደንቆሮ ሰውን እንደ አዳነ ።
በእንተ ዘከመ አብዝኆ ኅብስተ ዳግመ ።	ም ፰	ቍ ፩	ሁለተኛ እንጀራ እንደ አበረከተ ።
በእንተ ዘከመ ኀሠሡ ትእምርተ እምሰማይ ።		ቍ ፲፩	ከሰማይ ምልክትን እንደ ፈለጉ ።
በእንተ ብሑእ ፈሪሳውያን ።		ቍ ፲፭	ስለ ፈሪሳውያን እርሾ ።
በእንተ ዕውር ዘቤተ ሳይዳ ።		ቍ ፳፪	የሳይዳ ሰው ስለሚሆን ዕውር ።
በእንተ ተአምኖተ ጴጥሮስ ፤		ቍ ፳፯	ጴጥሮስ እንደ አመነ ።
በእንተ ትንቢት ዘሕማማት ፤		ቍ ፴፩	ጌታ ስለ መከራው ትንቢት እንደ ተናገረ ።
በእንተ ኀዲገ ርእስ ዘክርስቲያን		ቍ ፴፬	ክርስቲያን ሰው ራሱን ስለ መጣል ።
በእንተ ዘከመ ተወለጠ ራእዩ በደብረ ታቦር ።	ም ፱	ቍ ፩	በደብረ ታቦር የጌታ መልኩ እንደ ተለወጠ ።
በእንተ ዘከመ ሐይወ ዘአስተራገጾ ጋኔን ።		ቍ ፲፬	ጋኔን የሚያንዘፈዝፈው እንደ ዳነ ።
በእንተ ዘከመ አቅደመ ነጊረ መዊቶቱ ።		ቍ ፴	የሞቱን ነገር አስቀድሞ እንደ ተናገረ ።
በእንተ ትዕግሥት ወትሕትና ዘክርስቲያን ።	ምዕራፍ ፱	ቍ. ፴፪	ስለ ክርስቲያን ትሕትናና መታገሥ ።
በእንተ ዘከመ ይደሉ አጥፍኦተ ዕቅፍት ።		ቍ. ፵፩	ማሰናከያ ስለ ማጥፋት ።
በእንተ ዘከመ ተግኅሠ እም ኢየሩሳሌም ።	ም ፲	ቍ. ፩	ጌታ ከኢየሩሳሌም እንደ ሄደ ።
በእንተ ዘከመ ኢይደሉ ኀዲገ ብእሲት ወአውስቦ ካልዕት ።		ቍ. ፪	ሚስትን መፍታት ሌላይቱንም ማግባት እንዳይገባ ።
በእንተ ዘከመ ባረኮሙ ኢየሱስ ለሕፃናት እለ መጽኡ ኀቤሁ ።		ቍ. ፲፫	ጌታ ወደሱ የመጡ ልጆችን እንደ ባረካቸው ።
በእንተ ወሬዛ ባዕል ።		ቍ. ፲፯	ስለ ሀብታም ጕልማሳ ።
በእንተ ዕሤቶሙ ለእለ ይተልውዎ ለኢየሱስ ።		ቍ. ፳፰	ጌታን ስለ ሚከተሉ ሰዎች ዋጋ ።
በእንተ ካልዕ ትንቢት ዘሕማማት ።		ቍ. ፴፪	ስለ ጌታ መከራ ሁለተኛ ትንቢት ።
በእንተ ገሥጾ ትዝሕርት ዘደቂቀ ዘብዴዎስ ።		ቍ. ፴፭	የዘብዴዎስን ልጆች ትዕቢት ስለ መገሠጽ ።
በእንተ ዕውር ወልደ በርጤሜዎስ ።		ቍ. ፵፮	ስለ ዕውር የበርጤሜዎስ ልጅ ።
በእንተ ዘከመ ቦአ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ።	ም ፲፩	ቍ ፩	ጌታ ኢየሩሳሌም እንደ ገባ ።
በእንተ በለስ ዘተረግመት ።		ቍ. ፲፪	ስለ ተረገመች በለስ ።
በእንተ እለ ያረኵሱ ቤተ መቅደስ ።		ቍ. ፲፭	ቤተ መቅደስን ስለ ሚያሳድፉ ።
በእንተ ትውክልት ኀበ እምላክ		ቍ. ፳	ጌታን ስለ ማመን ።
በእንተ ተስእሎት ዘዮሐንስ መጥምቅ ።		ቍ. ፳፯	የዮሐንስን ነገር ስለ መጠየቅ ።
በእንተ እኩያን ዓቀብተ ወይን	ም ፲፪	ቍ. ፩	ስለ ክፉዎች ወይን ጠባቆች ።
በእንተ ዘከመ አመከርዎ ለኢየሱስ በውሂበ ዲናር		ቍ. ፲፫	ዲናር ስለመስጠት ጌታን እንደተፈታተኑት ፤
በእንተ ሰዱቃውያን ወትንሣኤ ሙታን ።		ቍ. ፲፰	ስለሙታን ትንሣኤና ስለሰዱቃውያን ፤

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ማርቆስ ።		የማርቆስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ቀዳማዊ ትእዛዝ ።	ቍ. ፳፰	ስለ መጀመሪያ ትእዛዝ ።
በእንተ ማስያስ ወልደ ዳዊት	ቍ. ፴፭	ስለ ማስያስ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ።
በእንተ መደልዋን ጸሐፍት ።	ቍ. ፴፰	ስለ ግብዞች ጸሐፊዎች ።
በእንተ ዘከመ ወደሳ ለመበለት ነዳይት በውኂቦታ ጸሪቀ ።	ቍ. ፵፩	ድኻዪቱን ሴት ገንዘቧን በመስጠቷ እንደ አመሰገናት ።
በእንተ ንስቲተ ቤተ መቅደስ ወኢየሩሳሌም ።	ምዕራፍ ፲፫ ፤ ቍጥር ፩	ስለ ቤተ መቅደስና ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስ ።
በእንተ ካልዕት ምጽዓቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው	ቍ. ፳፬	ስለ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ።
ዘከመ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት ይቅትልዎ ለኢየሱስ ።	ም ፲፬ ቍ. ፩	ጌታን ሊገሉት ሊቃነ ካህናት እንደ መከሩ ፤
በእንተ ዘከመ ረፈቀ በቢታንያ ለምሳሕ ።	ቍ. ፫	ጌታ በቢታንያ ለመብል እንደ ተቀመጠ ።
በእንተ ዘከመ ሜጦ ይሁዳ ።	ቍ. ፲	ጌታን ይሁዳ እንደ ሸጠው ።
በእንተ ደኅራት ድራር ወአስተዳልዎት ።	ቍ. ፲፪	ሁለተኛ እራት ስለ ማዘጋጀት ።
በእንተ ዘከመ ከሠተ ለሐዋርያት ዘያገብኦ ።	ቍ. ፲፰	የሚያሲዘውን ለሐዋርያት እንደ ገለጠላቸው ።
በእንተ ዘከመ ሠርዓ አኰቴተ ቍርባን ።	ቍ. ፳፪	የቍርባንን ምሥጢር እንደ ሠራ ።
በእንተ ዘከመ ኀደግዎ ሐዋርያት ለኢየሱስ ።	ቍ. ፳፯	ሐዋርያት ጌታን ጥለውት እንደ ሸሹ ።
ዘከመ ጸለየ በጌቴሴማን ።	ቍ. ፴፪	በጌቴሴማኒ እንደ ጸለየ ።
በእንተ ዘከመ አግብአ ለኢየሱስ ወዘከመ አኀዝዎ ።	ቍ ፵፫	ጌታን ይሁዳ አሳልፎ እንደ ሰጠው እንደያዙትም ።
በእንተ ዘከመ ቆመ ኢየሱስ በዐውድ ።	ቍ. ፶፫	ጌታ በሸንጎ እንደ ቆመ ።
በእንተ ክሕደተ ጴጥሮስ ።	ቍ. ፷፮	ጴጥሮስ እንደ ካደ ።
በእንተ ዘከመ አቀምዎ ለኢየሱስ ቅድመ ጲላጦስ ።	ም ፲፭ ቍ. ፩	ጌታን ከጲላጦስ ፊት እንዳቆሙት ።
ዘከመ አስተደኀርዎ ለኢየሱስ እምኀ በርባን ወኰነንዎ	ቍ. ፮	ጌታን ከበርባን ይልቅ እንደ ረገሙት እንደ ፈረዱበትም ።
በእንተ ዘከመ ተሣለቁ ላዕለ ኢየሱስ ።	ቍ ፲፮	በጌታ እንደ ዘበቱበት ።
በእንተ ዘከመ አጾርዎ መስቀሎ ።	ቍ. ፳	መስቀሉን እንደ አሸከሙት ።
በእንተ ዘከመ ተሰቅለ ኢየሱስ ፤	ቍ. ፳፬	ጌታ እንደ ተሰቀለ ።
በእንተ ጸዕሩ ወሞቱ ለኢየሱስ ፤	ቍ. ፴፫	ስለ ጌታ ጭንቅና ስለ ሞቱ ።
በእንተ ዘከመ ተቀብረ ኢየሱስ ፤	ቍ. ፵፪	ጌታ እንደ ተቀበረ ።
በእንተ ትንሣኤሁ ለኢየሱስ	ም ፲፮ ቍ. ፩	ስለ ጌታ ትንሣኤ ።
በእንተ ዘከመ አስተርአዮሙ ኢየሱስ ለብዙኃን ፤	ቍ. ፱	ለብዙ ሰዎች እንደ ተገለጠላቸው ።
በእንተ ዘከመ ፈነዎሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት ።	ቍ. ፲፬	ጌታ ሐዋርያትን እንደ ሰደዳቸው ።
በእንተ ዕርገቱ ለኢየሱስ ።	ቍ. ፲፱	ጌታ እንዳረገ ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል

ቅዱስ ሉቃስ እንደ ጻፈው ።

ብሥራት ሉቃስ ወንጌላዊ ፩ እም፸ወ፪ቱ አርድእት ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ሉቃስ ማለት ዓቃቤ ሥራይ ማለት ነው ቀድሞ ዓቃቤ ሥራይ ዘሥጋ ነበር ኋላ ግን ዐቃቤ ሥራይ ዘነፍስ ሁኑዋልና አንድም ትንሣኤ ማለት ነው ለስብከተ ወንጌል ይፋጠናልና አንድም መበሥር ማለት ነው ብሥራት መልአከን ይጽፋልና ይህ ቃል የሠለስቱ ምእት ነው ። ጥንተ ነገሩ እንደምን ነው ቢሉ እንደ ማቴዎስ ተርክ ፤ ዕፃ በፃ ብለው ተካፍለው ለማስተማር በሚወጡበት ጊዜ ለዮሐንስ ምድረ ጽርእ ደረሰችው ለሰብአ አርድእት ግን ዕፃ የላቸውም አንዱም ሁለቱም ሁነው እንዱን ሐዋርያ አንዱም ሁለቱም ሁነው እንዱን ሐዋርያ ተከትለው ይሄዳሉ ሉቃስም ዮሐንስን ተከትሎ ሂዷል መቄዶንያ የምትባል አገር ክፍሎ አስተምር ብሎ ሰጥቶታል፡ ከዚያ ገብቶ ጌታ ከፅንስ ጀምሮ ያደረገውን ተአምራት ያስተማረውን ትምህርት የሠራውን ትሩፋት ቢያስተምራቸው ከአምልኮተ ጣዖት ወደአምልኮተ እግዚአብሔር ከግብረ ኃጢአት ወደ ግብረ ጽድቅ ፤ተመለሱ እምነት ተጠመቁ ትምህርት ካልደረሰበት ለማድረስ ወጥቶ በሚሄድበት ጊዜ መኰንን እስክንድርያ ታኦፊ ይለዋል ባጠገብ ያለች አገር ናት እሱም በሱ ስብከት እምኑዋል ወንጌልን ጻፍልኝ ብሎት በዚህ ምክንያት ይጽፋል አንድም እንዳባትነቱ ከራሱ አንቅቶ ይጽፋል መዋዕለ ጽሕፈት ሐተታ እንደ ማቴዎስ ጸሐፍቱም ሁለቱ ከሐዋርያት ሁለቱ ከአርድእት ናቸው ሐዋርያት ጨርሰው እንዲጽፉት ያላደረገ ሁለቱን ከአርድእት ያጻፈ ስለምን ነው ቢሉ ሐተታ እንደ ማቴዎስ ጸሐፍቱንስ ከፍ ብሎ አምስት ስድስት ዝቅ ብሎ ሁለት ሦስት ያላደረገ ስለምን ነው ቢሉ ሐተታ እንደ ማቴዎስ ወንጌልሂ ብለህ ተርክ ይህን አርእስት ሠለስቱ ምእት ሰጥተዋል ፤ እንደ ማቴዎስ ተርክ ።

ምዕራፍ ፩ ።

፩ እስመ ብዙኃን እለ ወጠኑ ይንግሩ ወይምሀሩ በእንተ ግብር ዘአምኑ በላዕሌነ ።

፪ በከመ መሐሩነ እለ ቀደሙነ ርእዮቶ ወተልእክዎ ለቃሉ ።

፫ ወረትዓኒ ሊተኒ እትልዎ እምጥንቱ ወጥዩቀ ኵሎ በበመትልው ።

፬ እጽሐፍ ለከ አአዚዝ ታኦፊላ ከመ ታእምር ጥዩቀ በእንተ ኵሉ ኃይለ ነገር ትምህርተ ዘተመሀርከ ።

እስመ ብዙኃን እለ እኃዙ ሠሪዓ ዜና ግብር ዘንሕነ ጠየቅናሁ በከመ አይድኡነ እለ ቀደሙነ ወተልእክዎ ለቃል ለቃሉም ይላል ሊተኒ ረትዓኒ ካዕበ እጽሐፍ ለከ አአዚዝታ ኦፊላ ከመ ታእምር ኃይለ ነገር ትምህርተ ዘተመሀርከ በአማን ኪያሁ ይላል አጭር አብነት ብዙኃን ያላቸው ማቴዎስና ማርቆስ ናቸው ። ከአንድ ከወጣ ብዙ ማለት የመጽሐፍ ልማድ ነው ወውእቱ ዘአኀበረ ተሰናዕዎተ ኵሉ ዘአኮ ቀሊለ ይረከብ ሰብእ በኀበ ኮኑ አማልክት ብዙኃን ወአጋእዝት ብዙኃን በሰማይ ወበምድር እንዲል ። ሠሪዕ ጽሒፍ ሲል ነው ወወልደ ዕጓለ እመሕያውስ የሐውር በከመ ተሠርዓ በእንቲአሁ እንዲል ዜና ወንጌል ናት ሥነ ዜና ሀለዓለም እንዲል ግብር ተአምራት ነው ።

፩ እኛ የተረዳነው ተአምራቱን የምትናገር ወንጌልን ሊጽፉ የጀመሩ ብዙ ናቸው እኮን ።
በከመ አይድዑነ እለ ቀደሙነ

፪ ከኛ አስቀድሞ የነበሩ እንደ ነገሩን ፥ ወተልእክዎ ለቃል አካላዊ ቃልን ያገለገሉት ወወልደ ዕጓለ እመሕያውስ ኢመጽአ ከመ ይትለአክዎ ዘእንበለ ዳዕሙ ይትለአክ እንዲል ወተልእክዎ ለቃሉ ይላል ወንጌልን ያስተማሩለት ።ወመጠነ ተልእከኒ ሠናየ በኤፌሶን ለሊከ ተአምር እንዲል ። ወንጌልን ያስተማሩለት አስቀድሞ የነበሩ ሰዎች እንደነገሩን ።

፫ ሊተኒ ረትዓኒ ለኒያ ቀናቸው እጽፍልህ ዘንድ ለኔም ቀናኝ ፥ ፫ኛ ሁኖ ይጽፋልና አንድም ግን ከማን ስንፎ ብለው ወንጌልን ሊጽፉ የጀመሩ ብዙ ናቸው እኮን ለኒያ አልቀናቸውም ሥላሴ ባራቱ ኪሩቤል አምሳል አድርገውባቸው ሊተስ ለኔ ግን እጽፍልህ ዘንድ ቀናኝ አራተኛ ሁኖ ይጽፋልና ተራ ሳይሻ አንድም እስከ ብዙኃን መጻሕፍተ ሐዲሳትን ሊጽፉ የጀመሩ ብዙ ናቸው እኮን ለኒያ ቀናቸው ። ለኔም ቀናኝ መጽሐፈ ግብረ ሐዋርያትን ይጽፋልና አንድም ግን ከማን ስንፎ ብለው



መጻሕፍተ ሐዲሳትን ሊጽፉ የጀመሩ ብዙ ናቸው እኮን ለኒያ አልቀናቸውም ሥላሴ ምሥጢር ከልባቸው ነገር ካንደበታቸው ብርዕ ከጃቸው አናከና ውንላችሁ ብለዋቸው ሊተስ ለኔ ግን ቀናኝ ሥላሴ ምሥጢር ከልቡናየ ብርዕ ከእጄ ነገር ካንደበቴ አከናውነውልኝ ።

እእዚዝ ታእፊላ የተዛወረ ቀለም ነው ፊላታዖ ማለት ነው ።

፬ ሥዩም ጌናና የምትሆን መፍቀሬ አምላክ እጽፍልሕ ዘንድ ለኔ ቀናኝ ። ፊላ መፍቀሪ ማለት ነው ። ታእስ ማለት በመ እምላክ ነው ከመ ታእምር ኃይለ ነገር ። ያን እውነተኛ አድርገህ የተማርከውን የወንጌል ምሥጢር ትረዳ ዘንድ ። አንድም እበመ ብዙኃን እለ አኃዙ ይውጥኑ ወይጽሐፉ

ይንግሩ ወይምሀሩ ይግበሩ ወያንብሩ በእንተ ግብር ዘእምኑ በላዕሌነ በእንተ ነገር ዘንሕነ ጠየቅናሁ በከመ አይድኡነ እለ ቀደሙነ ወኮኑ ርእየቶ እምቅድም ወኮኑ እምቅድመ ይርእዩ ኵሎ ዘኮነ ወኮኑ ይርእዩ ኵሎ ዘኮነ ወተልእከዎ ለቃለ ፈቃዱ ለቃለ ፈቃድከ ወፈቀድኩ አትልዎ እምጥንቱ በበመትልው እስመ ኮንኩ እተልዎ ለኵሉ ግብር በኵሉ ግብር ወእጤይቆ በጥይቅና ሊተኒ ረትዓኒ

ካዕበ እጽሐፍ ለከ ለእጊዝ ለእኃዚ ታእፊላ ከመ ታእምር ጽድቀ ኃይለ ነገር ትምህርተ ዘተመሀርከ በአማን ኪያሁ ይላል ረጅም አብነት በኛ ስብከት ያመኑትን እኛ ወንጌልን የተረዳንበትን ተአምራቱን የምትናገር ወንጌልን ጽፈው አጽፈው ደጉሰው ማኅደር ሰፍተው ሊያኖሩ የወደዱ ብዙ ናቸው እኮን ፩ም በኛ ስብከት ያመኑትን ወንጌልን እኛ የተረዳንበትን ተእምራቱን ሊጽፉ የወደዱ ብዙ ናቸው እኮን ።

ይንግሩ ለመጣላቸው
ይምሐሩ ፤ ዙረው ።
ይግበሩ ፥ ለራሳቸው ።
ያንብሩ ለሌላው ።

በከመ አይድኡነ ከኛ አስቀድሞ የነበሩ እንደነገሩን ወኮኑ እምቅድም ርእዮቶ አስቀድሞ ያደሩለት ። ንፈቅድ ንርእዮ ለእግዚእ ኢየሱስ እንዲል ወኮኑ እምቅድም ይርእዩ ይላል ፥ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር የሚያደርገውን ተእምራት ያዩ ዘንድ ያደሩለት ። ወኮኑ እምቅድመ ይርእዩ ኵሎ ዘኮነ ፥ ሠላሳ ሦስት ዓመት የሚደረገውን ታምራት ሳያዩ ያደሩለት ወተልእከዎ ለቃለ ፈቃዱ ፤ ወደ የሠራት ። ለቃለ ፈቃድከ ይላል ወደህ የተቀበልካት ወንጌልን ያስተማሩለት ወፈቀድኩ እትልዎ እምጥንቱ በመትልው በጀመረበት በጀምር በጨረሰበት በጨርስ የሚቀድመውን ሳስቀድም የሚከተለውን ሳስከትል በጽፈት ልከተለው ወደድኩ ኀበሂ ዓርገ ደብረ ወኀበሂ ነበረ ወኀበሂ መሐረ ኀበሂ ዓርገ ሐመረ ወኀበሂ ገሠጸ ባሕረ እንዲል ከሁሉ ይልቅ ሉቃስ ተራ ያቀናል ይባላልና እስመ ኮንኩ እተልዎ ለኵሉ ግብር ሥራውን ሁሉ እማርለት ነበርና እንተስ ተለውከ ትምህርተየ እንዲል አንድም በጀመረበት በጀምር በጨረሰበት በጨርስ የሚቀድመውን ሳስቀድም የሚከተለውን ሳስከትል ልጽፈው ወደድኩ እስመ ኮንኩ እተልዎ በኵሉ ግብር ይላል በሥራው ሁሉ እመስለው እከተለው ነበርና ።

ሊተኒ ረትዓኒ ካዕበ እጽሐፍ ለከ ለእጊዝ በአጋንንት ለመሠልጠን ለእኃዜ ሥልጣና ለምትሆን ላንተ ታየፊላ ሆይ ዳግመኛ እጽፍልሕ ዘንድ ለኔም ቀናኝ። ከመ ታእምር ጽድቀ ኃይለ ነገር ፥ ያን እውነተኛ አድርገህ የተማርከውን የወንጌልን ምሥጢር መረዳትን ታውቅ ዘንድ ።

በከመ አይድዓ ገብርኤል ልደቶ ለዮሐንስ.

፭ ወኮነ በመዋዕለ ሄሮድስ ንጉሥ ሀሎ አሐዱ ካህን ዘስሙ ዘካርያስ በመዋዕለ አብያ ፩ ኀጹ ፳፬ ፲። ኮነ ያለውን ሀሎ ብሎ አመጣው ።

፭ ፤ ሄሮድስ ነግሦበት በነበረ ዘመን አብያ ሊቀ ካህናትነት በተሾመበት ወራት ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበር ፥ አብነት ዘአምዘመደ አብያ ይላል ። ከአብያ ዘመዶች ወገንን የሚሆን ዘእምላእካነ ቤተ አብያ ይላል ። ከአብያ ወገን ተሹመው ከሚያገለግሉት ወገን የሚሆን ።

ወይሠርጽ ከመ ሕገ ቤተ አብያ

ከአብያ ወገን እንደሚሠሩት ሥራ የሚሠራ ሐተታ ተራ ካህን ነው ቢሉ የተመቸ ሊቀ ካህናት ነው ቢሉ ምሉና ደግ ሁነው ተሹመው ነበርና ወብእሲቱኒ እምእዋልደ አሮን

ሚስቱም ከእዋልደ አሮን ወገን ናት ።

ወስማ ኤልሳቤጥ

ስሟም ኤልሳቤጥ ትባል ነበረ ሐተታ የአሮን ሚስት ኤልሳቤጥ ሳለች ኦሪት ተሠርታለች የዘካርያስ ሚስት ኤልሳቤጥ ሳለች ወንጌል ተሠራች ። በኤልሳቤጥ የተሠራች ሕግ በኤልሳቤጥ አለፈች ለማለት

፮ ወከልኤሆሙ ጻድቃን እሙንቱ በቅድመ እግዚአብሔር ።

፮ እግዚአብሔር ባወቀው ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ሁለቱም ሁሉ ደጋግ ነበሩ ።

ሐተታ እበመ መካን ይእቲ ኤልሳቤጥ ብሎ እንደሚያመጣው ምክንያት በኃጢአት አይደለውምን ምክንያትስ ኢተውህበ ለብእሲት ዳዕሙ በግብረ እደ ሃ ትመጥት ዘእንበለ ውሉድ እንዲል ጻድቃን ማለቱ እንደምን ነው ቢሉ በሌላው እውነት ነው እኒን

ግን መካን ማለቱ እስክትወልድ ድረስ ነውና ።
ወየሐውሩ በኵሉ ትእዛዙ ።
በትእዛዙ ጸንተው ይኖራሉ ወነበቦ ባሰው
ወሕጉ
በዘጠኙ ቃላት
ወዙንኔሁ ለእግዚአብሔር ።
በኢታምልክ ጸንተው ይኖራሉ ።
ወንጹሐን እሙንቱ እምኃጢአት ።
ከሩካቤ ንጹሐን ናቸው ።
ሐተታ ይህንስ ኃጢአት አይለውም ቅዱስ ጳውሎስ ክቡር አውስቦ ብሎታል ብሎ ከሌላው ኃጢአት ንጹሐን ናቸው ።

፯ ወአልቦሙ ውሉድ ።
፯ ልጅ አልነበራቸውም ።
እስመ መካን ይእቲ ኤልሳቤጥ
ኤልሳቤጥ መካን ነበረችና ።
ወክልኤሆሙ ልኂቃን እሙንቱ ።
እሷም እሱም አርጅተው ነበርና
ወኃለፈ መዋዕሊሆሙ
የሕፃንነታቸው ዘመን አልፎባቸው ነበርና ።

፰ ወእምዝ እመ ይገብር ግብረ ክህነት በዕብሬቱ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፰ በከመ ይገብሩ ካህናት ።

፱ ከዚህ በኋላ ካህናቱ እንደሚሠሩት ሥራ ያስ በቤተ መቅደስ ሁኖ ፥ ተራ ካህን ነው ቢሉ በስሞኑ ሊቀ ካህናት ነው ።

፱ ቢሉ ባመት ፩ ቀን ፥ የክህነት ሥራ በሚሠራበት ጊዜ ። በጽሐ ጊዜ የዐጥን ።
የሚያጥንበት ጊዜ ደረሰ ። ሐተታ ለእግዚአብሔር ሁሉ ፊቱ ሲሆን መሥዋዕት የተሠዋበትን ስሙ የተጠራበትን ቅድመ እግዚአብሔር ይለዋል ።
ወቦአ ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ።
ከቤተ መቅደስ ገባ ። ታሪክ የጥቅምት ጨረቃ ሠርቅ ባደረገች ባሥር ነው ፥ ዕለቱም ዕለተ ዮሴፍ ነው ፥ ተሰብስበው ይጸልያሉ ። ወበይእቲ ዕለት አሕምምዋ ለነፍስከሙ እንዲል አባቶቻቸው በኮሬብ ዕንላተ ላሕም አቁመው ነበርና ። ሮቤል ካባቱ ቁባት ደርሶ ነበርና አንድም ወንድማቸውን ዮሴፍን ሸጠው በልተው ነበርና በዚህ ሁሉ እዳ አታድርግባቸው ሲሉ ፥

፲ ወኵሎሙ ሕዝብ ሀለዉ በምልእሙ ይጼልዩ በአፍአ በጊዜ ሰዓተ ዕጣን ። ዘፀ.፴፥፯ ፥ ዘሌ. ፲፮፥፲፯ ።

፲ ሕዝብ ሁሉ በሚያጥንበት ጊዜ ተሰብስበው በአፍአ ይጸልዩ ነበር ። ሐተታ ፥ ምን እያሉ ይጸልዩ ነበር ቢሉ በጕ ራዕይ ግለጽለት ስቡን ፀእ ቅርንተ ምሥዋዕ ምላለት እያሉ ስቡ የመላ እንደ ሆነ ዘመነ ጽጋብ ይሆናል የጐደለ እንደሆነ ዘመነ ረኃብ ይሆናል ። አንድም ዓብዩድን ናዳብን ባላወቁት ኃጢአታቸው እንደ ቀሰፍካቸው ባላወቀው ኃጢአቱ አትቅሠፈው እያሉ ።

፲፩ ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር እንዘ ይቀውም መንገለ የማነ ምሥዋዕ በዕጣን ዘበርትዕ አለና ከዚያ ሲለይ ።

፲፩ ዕጣን አለ በመሠውያው ቀኝ በኩል ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ታየው ። ሐተታ ፥ ለሰይጣን ቀኝ የለውም ። መልአክማን የማናዊ ነውና መልአክ እንደሆነ ለማጠየቅ በቀኝ በኩል አለ ፩ም ሰው ሁሉ ወደ የማናዊ ግብር የሚመለስበት ዘመን ደረሰ ሲል ፩ም ሰውን ሁሉ መክሮ አስተምሮ ወደቀኝ የሚመልስ ልጅ ትወልዳለህ ሲል ።

፲፪ ወሶበ ርእዮ ደንገፀ ዘካርያስ
፲፪ ዘካርያስም መልአኩን ባየው ጊዜ ደነገጠ ፍርኃት ወረዳ ወረደ ላዕሌሁ ፍርኃት ረዓድ አደረበት ፥ ሐተታ ፍርሃት የልቡና ረዓድ የጉልበት ድንጋፄ የናላ ነው ልማድ ቢሰወጥበት ከዚህ አስቀድሞ ከምስሐል ከአዕናቍ ቃል ይሰማ ነበር ።
እንጂ መልአክ አይቶ አያውቅምና ።
አንድም አብዩድን ናዳብን ባላወቁት ኃጢአት እንደ ቀሠፋቸው ባላወቅሁት ኃጢአቴ ሊቀሥፈኝ መጣ ብሎ አንድም አጀም ያስፈራ ነበርና በአፍአ ያሉትን ጨርሶ እኔንም ሊገለኝ መጣ ብሎ ፥

፲፫ ወይቤሎ መልአክ ኢትፍራህ ዘካርያስ
፲፫ መልአኩ ዘካርያስን አትፍራ አለው ።
ሐተታ ፥ ፍርኃት አርቆ መናገር ለመልአክ ልማዱ ነውና ፥ ኢትፍራህ ብእሴ ፍትወቶ ዳንኤል ኢትፍርሂ ማርያም እንዲል ፤ እስመ ናሁ ተሰምዓ ጸሎትከ ቅድመ እግዚአብሔር ።

ልጅ ስጠኝ እያለ ይለምን ነበር ቢሉ ልመናህ ተሰምቷልና ብእሲትከ ኤልሳቤጥ ትፀንስ ወትወልድ ለከ ወልደ ።

ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ አንድም እሪት የተማረ ነበርና የተቈጠረው ሱባዔ ደረሰ የተነገረው ትንቢት ቀረ እያለ ይጸልይ ነበርና ልመናህም ተሰምቷልና ወብእሲትከኒ ሚስትህም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች አለው ወትሰምዮ ስሞ ዮሐንስ ።

ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ዮሐንስ ማለት ፍሥሓ ወኃሤት ማለት ነው ።

፲፬ ወይከውነከ ትፍሥሕተ ወኃሤተ
፲፬ ፈጽሞ ደስ ያሰኝሃል ።
ወብዙኃን ይትፌሥሑ በልደቱ በመወለዱም ብዙ

ሰዎች ደስ ይላቸዋል ወሶበ ሰምዑ አዝማዲሃ ወአግዋሪሃ ከመ አዕበየ እግዚአብሔር ሳዕሌሃ ሣህሎ ተፈሥሑ ባቲ እንዲል እንድም በትምህርቱ በትንቢቱ ደስ ይላቸዋል ።

፲፭ እስመ ዓቢየ ይከውን ወእቱ በቅድመ እግዚአብሔር ።

፲፭ በእግዚአብሔር ዘንድ ደግ ይባላልና ።
ኢይሰቲ ወይነ ወሜሰ ።
የወይን ጠጅ የማር ጠጅ አይጠጣም ። ሐተታ የማር ጠጅስ በሀገራቸው እጅግም ያሀል ብሎ ጥሩ ጠጅ ጉሽ ጠጅ አይጠጣም ኢዘያሰክር ። አረቄ
ወኢዘኢያሰክር ።
ቡን አይጠጣም ፤
ይመልእ ላዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ እምከርሠ እሙ።
ከናቱ ማኅፀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ተመልቶ ይኖራል ።

፲፮ ወለብዙኃን እምደቂቀ እስራኤል ይመይጦሙ ኀበ እግዚአብሔር አምላኮሙ ፤

፲፮ መክሮ አስተምሮ ከእስራኤል ወገን ብዙ ሰዎችን ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ይመልሳቸዋል ፤

፲፯ ወውእቱ የሐውር ቅድሜሁ ። በመንፈስ ቅዱስ ሚልክ. ፬ ፣ ፮ ፣ ማቴ ፣ ፲፩ ፣ ፳፬ ።

፲፯ በፊት በፊት ይሄዳል ማለት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ መንፈቅ ተቀድሞ ያስተምራል ።
ወበኃይለ ኤልያስ ።

በኤልያስ ግብር ጸንቶ ይኖራል ። እንድም በመንፈስ ቅዱስ ኃይለ ኤልያስ ኤልያስ ተቃኝቶበት በሚኖር በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ይኖራል ።
ከመ ይሚጥ ልበ አበው ኀበ ውሉድ ።
የአበው የነአብርሃምን ዕውቀት ወደ ውሉድ ወደ ሐዋርያት ይመልስ ዘንድ ።

ወሕሊና ከሀድያን ኀበ አእምሮ ጻድቃን ።
የከሀድያን የነ አብርሃምን አእምሮ ወደ ጻድቃን ወደ ሐዋርያት አእምሮ ይመልስ ዘንድ ሐተታ ከሀድያን አላቸው በቀደመ ግብራቸው እንድም የአበው የጸሐፍት ፈሪሳውያን ዕውቀት ወደ ውሉድ ወደ ሐዋርያት ዕውቀት ይመልስ ዘንድ ፣ የከሀድያን የፈሪሳውያንን አእምሮ ወደ ውሉድ ወደ ሐዋርያት አእምሮ ይመልስ ዘንድ አሁን የተመቸ ።
ከመ ይሥራዕ ሕገ ።
ሥራት ይሠራ ዘንድ ።
ወሕዝበ ዘድልው ለእግዚአብሔር ።
ሕዝቡን መክሮ አስተምሮ ለእግዚአብሔር ማኅደር ለመሆን የበቁ ያደርግ ዘንድ ።

፲፰ ወይቤሎ ዘካርያስ በምንት አአምር ከመ ይከውን ዝንቱ ዙሉ ።

፲፰ ዘካርያስም ይህ ሁሉ እንዲደረግ በምን ዐውቀዋለሁ አለው ሐተታ ምልክት ሽቶ እስመ አይሁድኒ ተእምረ ይሴዓሉ እንዲል እንድም ተጠራጥሮ ። ናሁ አነ ልሂቅ ።
እነሆ እኔ አርጅቻለሁ ።
ወብእሲትየኒ ኃለፈ መዋዕሊሃ የሷም የሕፃንነቷ ዘመን አልፏዋል ።

፲፱ ወተሰጥዎ መልአክ ።
፲፱ መልአኩም መለሰ ።

ወይቤሎ አነ ውእቱ ገብርኤል ዘእቀውም ቅድመ እግዚአብሔር ዘተፈኖኩ ኀቤከ እንግርከ ወእዜንከ ዘንቱን ልደቱን ልነግርህ መዳንተ የተላከሁ የእግዚአብሔር ባለሟል የምሆን እኔ ገብርኤል ነኝ አለው ። ሐተታ የእግዚአብሔር ባለሟል ያይደለ ሰይጣን ሐሰት ይናገራል እንጂ የእግዚአብሔር ባለሟል የምሆን እኔ ሐሰት እናገራለሁን ለማለት እንዲህ አለ ። ሐተታ በምን ያውቀዋል ቢሉ በመጽሐፍ በሄኖክ በዳንኤል ሲመለከት ለምዶታልና።

፳ ወናሁ ትከውን በሐመ ።
፳ ምልክት ሽቶ ላለው ለዚህ ምልክት ድዳ ትሆናለህ ። ወትስእን ነቢበ እስከ እመ ይከውንዝንቱ ይህ እስኪደረግ ድረስ አትናገርም ።
እስመ ኢአመንከኒ ነገርየ ዘይከውን ወይትፌጸም በዕድሜሁ በጊዜው ጊዜ የሚደረግ ነገሬን አልተቀበልሽኝምና ። እንድም ተጠራጥሮ ላለው የተግሣጽ አነጋገር ።
እመ ኢአመንከኒ ።
በጊዜው ጊዜ የሚደረግ ነገሬንስ ካልተቀበልከኝ ድዳሁን እትናገር አለው ።

፳፩ ወሀለዉ ሕዝብ ይጼልዩ ወይጸንሕዎ ለዘካርያስ ።
፳፩ ሕዝቡ ግን ይመጣል እያሉ እየጠበቁት ይጸልዩለት ነበር ።
ወአንከሩ ።
አደነቁ ራዕይ በስቶበትን ይሆን አረጋዊ ነውና ወድቆ የሚያነሣው አጥቶ ይሆን አብዩድን ናዳብን ባላወቁት ኃጢአታቸው እንደ ቀሰፋቸው ባላወቀው ኃጢአቱ ቀሥፎት ይሆን እያሉ
እስመ ጐንደየ ውስተ ቤተ መቅደስ ።
ቤተ መቅደስ ከገባ ብዙ ሰዓት ሁኖታልና ።
፳፪ ወወፂኦ ኀቤሆሙ እፎአ ስእነ ተናግሮቶሙ
፳፪ ወደነሱ በወጣ ጊዜ መናገር ተሳነው ።
ወአእመሩ ከመቦ ዘአስተርአዮ ውስተ ቤተ መቅደስ በቤተ መቅደስ ሳለ የታየው እንዳለ ዐወቁ የታየው አለ አሉ ።

ወነበረ ከማሁ እንደ በህም ውእቱ ።
ወኩን በህመ ወሰአን ነቢበ እንዳለው ድዳ ሁኖ ኖረ ።
ወይኤምርሙ በእዴሁ ።
ተርታውን ነገር በእጁ እየጠቀሰ ያሳያቸው ነበር እንድም አይነተኛውን እየጻፈ ስምዖን የሚባል ተወራጅ ሹሞላቸው ኖረ ።

፳፫ ወእምዝ ፈጺሞ መዋዕለ ዕብሬቱ አተወ ቤቶ ።

፳፫ ሊቀ ካህናት ነው ቢሉ በዓመት አንድ ቀን አጥኖ ከከተማ ቤቱ ገባ ። ተራ ካህን ነው ቢሉ ስሞኑን ፈጽሞ ዓርገ ደብረ ዘይት ይላል ደብረ ዘይት ወዳለ ቤቱ ገባ ።

፳፬ ወእምድኅረ ክልኤ መዋዕል ፀንሰት ኤል ሳቤጥ ብእሲቱ ።

፳፬ ከሁለት ቀን በኋላ ኤልሳቤጥ ፀነሰች ። ሐተታ ስለ ክብረ ዕጣን ሁለት ቀን ኑሮ ተገናኝቷታል ። ዛሬም ሕጋውያን ስለ ሥጋው ደሙ ሁለት ቀን ኑረው መገናኘት ይገባቸዋል ።

፳፭ ወከበተት ፅንሳ ኃምስተ አውራኃ እንዘ ትብል ከመዝኑ ረስየኒ እግዚአብሔር አመ ሐውፆ ሐወፀኒ በዝንቱ መዋዕል ያዕትት ዝንንጌየ እምሰብእ

፳፭ በዚህ ወራት ስድቤን ከሰው ያርቅልኝ ዘንድ እግዚአብሔር በረድኤት በጐበኘኝ ጊዜ እንዲህ አደረገኝ ብላ አምስት ወር ፅንሷን ሰወረች ። ሐተታ ፣ በደግ ሴት ልማድ ዳግመኛ ይህች ባልቴት የበላችው ቂጣ ቢነፋት ፀነሰኩ ትላለች ባሏት ነበርና ምን እያሉ ይሰድቧት ነበር ቢሉ ዕጹተ ማኅፀን ይብ ሰተ እጥባዕት ኅጥእተ በረከት ምልእተ መርገም የበቅሎ ዘመድ ቢወልዷት እንጂ አትወልድ እያሉ ይሰድቧት ነበርና ።
በእንተ ዘአብሠራ ለማርያም ወበእንተ ሥጋዌሁ ለቃል ።

፳፮ ወበሳድስ ወርኅ ተፈነወ ገብርኤል መል አከ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ አሐቲ ሀገር ዘገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት ።

፳፮ ወከበተት ፅንሳ ፭ተ አውራኃ ብሎ ነበርና በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል የገሊላ ክፍል ዕፃ ወደምትሆን ናዝሬት ወደምትባል አገር ከእግ ዚአብሔር ዘንድ ታዞ ሄደ ።

፳፯ ኀበ ድንግል እንተ ተፍኅረት ለብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ ዘእምቤተ ዳዊት ።

፳፯ ከዳዊት ወገን ለተወለደ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደታጨች ወዳንዲት ድንግል ። ሐተታ ብዙ ገሊላ አለና ከዚያ ሲለይ እንተ ስማ ናዝሬት ብዙ ደናግል አሉና እንተ ተፍኅረት ለብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ ብዙ ዮሴፍ አለና ከዚያ ሲለይ ዘእምቤተ ዳዊት አለ ። ወስማ ለይእቲ ድንግል ማርያም ።

ያችም ብላቴና ማርያም ትባላለች ታሪክ ነገረ ማር ያም የተፍኅርስ ነገር እንደምን ነው ቢሉ ተከታ በጥሪቃ የሚባሉ ባለጸጎች ባልና ሚስት ነበሩ ባለጸግነታቸውም የወርቅ የዕንቍ የወንድ ባሪያ የሴት ባሪያ የፈረስ የበቅሎ የላም የበግ የፍየል ይህ ቀራ ቸው የማይባሉ ነገር ግን ልጅ አልነበራቸውም ከዕለታት ባንድ ቀን ከዕቃ ቤት ገብቶ ዕቃውን አይቶ ቴክታ ካንች በቀር የምወደው እንደሌለኝ አምላክ እስራኤል ያውቃል ነገር ግን ልጅ የለንም አላት ። ለልጅማ እኔ ምንድነኝ ወደ እግዚአብሔር እናመልክት እንጂ አለችው እመለከቱ ፤ ነጭ እን ቦሳ ከማኅፀንዋ ስትወጣ ። እንቦሳዋ እንቦሳ ስትወ ልድ እስከ ሰድስት ድረስ ፯ተኛይቱ ጨረቃ ጨረ ቃይቱ ፀሐይ ስትወልድ አይታ ነገረችው ፣ በዘመ ናችው መተርጕመ ሕልም አለና ሄደህ አስተርጕመህ ና አለችው ሄዶ ቢነግረው ደግ ልጅ ትወልዱ ይሆ ናል አለው ። ተመልሶ መጣ ምን አለህ አለችው ልጅ ትወልዱ ይሆናል አለኝ አላት ። የጨረቃይ ቱንና የፀሐዩንስ ጊዜ ይተርጕመው እንጂ አልተተ ረጐመም አለችው እንዲህ ሁነው ሲኖሩ ፀነሰች ወለደችም ስሟንም ሄኤሜን አለቻት ረከብኩ ስእ ለትየ ማለት ነው ሄኤሜን ደርዲዕን ደርዲዕ ቶናህን ቶናህ ሲካርን ፣ ሲካር ሄርሜላን ሄርሜላ ሐናን ወለደ ሐና ከነገደ ይሁዳ የተወለደ ኢያቄም የሚ ባል ሰው አግብታ መካን ሁና ስትኖር ወዳጅ ባል ንጀራ አለቻት ዛሬ ከቤተ እግዚአብሔር ሄጂ እጅ ልንግባ እወዳለሁ ነገር ግን ልብስ የለኝም እንጂ አለቻት የኔ ልብስ ብዙ አለልሽ አንዱን ለብሰሽ ሂጂ አለቻት ምን አልባት በዝሙት ያመጣሽው እንዳይ ሆን አለቻት እግዚአብሔር በምን ምክንያት ነው ልጅ የነሣሽ እያልኩ ሳዝንልሽ እኖር ነበር ለካ ብት ዕቢትሽ ነው አለቻት ነገሩም አልቀረም ተውሳ ለብሳ እጅነሥታ ስትመለስ አርጋብ ከመንገድ ሁነው ከል ጆቻቸው ጋራ ሲጫወቱ አይታ ለሁሉ ልጅ ስጥተ ኸዋል ሐናን ደንጊያ ብለህ ፈጥረሃታልን ብላ አል ቅሳ ተመለሰች በዚህ ሌሊት ጸዓዳ ርግብ ሰባቱን ሰማያት ሰንጥቃ መጥታ በማኅፀንዋ ስታድር ለኢያ ቄም የፀምር መታጠቂያ ሲያስታጥቁት የብርሃን በትር ሲያሲዙት ዓይታ ነገረችው እሱም እኔም እንጂ ከደጃችን ያለች ዛፍ ለምልማ አብባ አፍርታ ፍጥረት ሁሉ ሲመገባት አየሁ ብሎ ነገራት ። ከዚህ በኋላ እመቤታችን ተፀነሰች ።

ሮቤል የሚባል ዘመዷም ወዳጅዋም ቢሉ ሞተ ትወደው ነበርና ያልጋውን ሸንኮር ይዛ ስታለቅስ የሞተው ተነሥቶ ሰላም ለኪ አ እምኔውቱ ለፀሐየ ጽድቅ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ ብሎ ለመተርጐመ ሕልም ያልሆነለትን ተርጕሞ አርፏል ። አይሁድ ይህን ሰምተው ምቀኝነት አደረባቸው ፤ ቀድሞ ከኔህ ወገን ዳዊት ሰሎሞን እየተወለዱ አርባ አርባ ዘመን ገዙን ዛሬ ደግሞ ከኔህ የሚወለድ እንደምን ያለ ይሆን ብለው ቀኑባቸው ኋላ እመቤታችን ተወሰደች ሦስት ዓመት ሲሆናት መዋዕለ ጥብ ቢፈጸም የብፅዓት ልጅ ናትና ወስደው ለካህናት ሰጡ ካህናቱም አክብረው ተቀብለው የምግቧን ነገር እንዴት እናደርጋለን ሲሉ ፤ መልአኩ ፋኑኤል ሰማያዊ ኅብስት ሰማያዊ ጽዋ ይዞ ወረደ ዘካርያስ የኔ ሀብት ነው ብሎ ሊቀበል ሄደ ሽቅብ ይዞት ወጣ ሲመለስ ይወርዳል ፤ ሁሉም የኛ ሀብት ነው እያሉ ቢሄዱ ሽቅብ እየያዘው እየወጣ የማይሆን ሆነ የዚች ብላቴና ሀብት እንደሆነ ከሰው ለይተሽ አኑረሻት ነይ አሏት ። ከሰው ለይታ አኑራት ብትሄድ ከምድር ሦስት ክንድ ተስንዝር ከፍ አድርጎ ከንቶን ጋርዶ መግቧት ዓረገ ። በዚህ ሁሉ ምቀኝነት አድሮባቸዋል ። የምግቧስ ነገር ከተያዘልን ብለው ከቤተ መቅደስ አኖሯት ። ሴሲት እንግዲያስን እያሉ ይመጣሉ የቤተ መቅደሱ ቅጽር እሳት እየሆነ ይመልሳቸዋል

መጥቁል የሚባል መሠርይ አለ እንዲህ ያለችጠላት ተነሥታብናለችናእጥፋልንብለው ብዙ ወርቅ ብዙ ግምጃ ብዙ ከብት ሰጡት ወርቁን ብረት ብሩን ብርት አደረገችው ። ግምጃውን ብል በላው ደመ ነፍስ ያላቸው ሁሉ አልቀው አድረዋል ። እንዲህ ያለች ናት ሐሰት መሰሎኝ ብሎ ሦስት መቶ ልብሳን ሥጋ አጋንንት በምስሐብ ስቦ እንዲህ ያለች ጠላት ተነሥታብናለችና አጥፋልኝ አላቸው ፤ እንተማ ወዳጆችን ስትለን ሰማዩን ምድር ምድሩን ሰማይ አድርጉ ብትለን ይሆንልን የለምን ብለው ተሰብስበው መጡ ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከመንገድ ቆይቶ በሰይፍ አርዶ አርዶ ፈጅቷቸዋል በቤተ መቅደስ ዐሥራ ሁለት ዓመት ትኖራለች ፤ ከዚያ ሦስት ዐሥራ አምስት ዓመት ይሆናል ። አይሁድ ለምቀኝነት እያርቁምና ይህች ብላቴና መጠን አንስት አደረሰች ቤተ መቅደስ ታሳድፍብናለች ትውጣልን አሉት ዘካርያስን ሊቀ ካህናቱ እሱ ነውና እንደምን ትሆኝ አላት ወደ እግዚአብሔር አመልክትልኝ አለችው ቢያመለክት ከነገደ ይሁዳ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን ሰዎች በትር ሰብስበህ ከቤተ መቅደስ አግብተህ ጸልይበት ምልክት እገልጽልሃለሁ አለው ። ቢሰበስብ ሽህ ከዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ሆነ ለሁለት ሽህ ዐሥራ አምስት የጎደለው ማለቷ ነው ያን ከቤተ መቅደስ አግብቶ ቢያወጣው ከዮሴፍ በትር አዮሴፍ ዕቀባ ለማርያም የሚል ተቀርጾ ተገኝቷል ። ርግብም መጥታ ከራሱ ላይ አርፋበታለች ፤ ዕጣም ቢያወጡ ለሱ ወጥቷል እንደ ሦስት ምስክር ያም ሆነ ያም ሆነ ከእግዚአብሔር አግኝተን የሰጠንህን ከእግዚአብሔር አግኝተን እስክናስናብትህ ወስደህ ጠብቃት አትንካ ብለው ሰጡት የተፍገሮ ነገር ይህ ነው ። ማርያም ማለት መርሀ ለመንግሥተ ሰማይ ማለት ነው ። ምእመናንን እየመራች ገነት መንግሥተ ሰማይ ታገባለችና ። አንድም ፍጽምት ማለት ነው ለጊዜው መልክ ከደም ግባት አስተባብራ ይዛ ተገኝታለች ። ፍጻሜው ግን ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና አንድ አድርጋ ይዛ ተገኝታለችና አንድም ጸጋ ወሀብት ማለት ነው ለጊዜው ለናት ላባቷ ጸጋ ሀብት ሁና ተሰጥታለች ። ፍጻሜው ግን ለሁላችን ተሰጥታለችና ። አንድም ልዕልት ማለት ነው አርያም ማለት ልዑል ማለት እንደሆነ እመቤታችንንም መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ይላታልና ። ተፈሥሒ ቤተ ይሁዳ ወተሐሠዪ ቤተ እስራኤል ተሰአኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ ማንበረ መሃይምናን ወሕዝብ ማለት ነው ። አንድም ማሪሃም ማለት እግዝእተ ብዙኃን ማለት ነው አብርሃም ማለት አበ ብዙኃን ማለት እንደሆነ ያንም ዘበዕብራይስጢ እንጂ ይለዋል ብሎ ማርያም ማለት ትሉ እግእዝተ ብዙኃን ማለት ነው ።

፳፰ ወቦአ መልአክ ኀቤሃ

፳፰ መልአኩ እሷ ወዳለችበት ቤት ገባ የቦታ አንድም ባሕርዩዋን መስሰላት መስሎ ታያት ። ወይቤላ ተፈሥሒ ፍሥሕት አምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ።
እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይሆናልና በትንቢተ ነቢያት በመላእክት ተልእኮ ደስ ያለሽ ምልእተ ክብር ሆይ ደስ ይበልሽ አላት ።
ወቡርክት አንቲ እምአንስት ።
ከሴቶች ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ ነሽ ።

፳፱ ወርእያ ደንገፀት እምቃሉ ።

፳፱ መልኩን አይታ ድምፁን ሰምታ ደንገፀች ። አንድም ርእያ ቅሉ ሰሚዓ ሲል ነው ወርእዮ ሕልመ አቡሁ ገብአ ማቴሳላ እንዲል ። ድምፁን ሰምታ ደንገጠች ።
ወኀለየት ወትቤ አፎኑ ዘከመዝ እንጋ አምኃ ይትአምኅ እንዴት እንዲህ ያለ ሰላምታ እንደምን ይቀበላሉ ብላ አስባ ተናገረች ። ሐተታ ፤ እናቴን ሄዋንን ያሳተ ሰይጣን ሊያስተኝ መጥቷል ብላ ።

፴ ወይቤላ መልአክ ኢትፍርሂ ማርያም ።
፴ መልአኩም ማርያም አይዞሽ አትፍሪ አላት ሐተታ ፣ ለመልአክ ፍርኃት አርቆ መናገር ልማድ ነውና ። ኢትፍራህ ብእሴ ፍትወት ዳንኤል ኢትፍራህ ዘካርያስ እንዲል ።
እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር ።
በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና

፴፩ ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ። ኢሳ ፯፣ ፲፬ ሉቃ ፪፣ ፳፩

፴፩ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ።
ወትሰምዪዮ ስሞ ኢየሱስ ።
ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ

፴፪ ውእቱ ዓቢይ ። ዳን. ፯፣ ፲፬ ።
፴፪ እሱ ዓቢይ እግዚአብሔር ነው
ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ።
የልዑል የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ይባላል
ወይሁቦ እግዚአብሔር መንበረ ዳዊት አቡሁ ።
እግዚአብሔር አብ ያባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ። ሐተታ ፣ ይህማ የተነገረ ለሰሎሞን አይደለም ቢሉ ለጊዜው ለሰሎሞን ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ ነውና ። አንድም ሰሎሞን በግዘፍ በነገሠባቸው ጌታ በርቀት ይነግሥባቸዋልና አንድም የጌታ መንግሥቱ መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም ብሎ በተናገረለት ሥልጣን ነውና አንድም ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምዒ ብሎ መንበር አድርጎ በተናገረለት በምእመናን ላይ ነውና አንድም ነገሠ መባሉ ቅሉ በሥጋ ዳዊት ነውና ዲበ መንበረ ዳዊት ትፀንእ መንግሥቱ እንዲል ።

፴፫ ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም ።
፴፫ በያዕቆብ ወገን ለዘለዓለም ሠልጥኖ ይኖራል ።
ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ ።
ለጌትነቱ ፍጻሜ የለውም ።
ወርኢኩ በራዕየ ሌሊት ወመጽአ ከመ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ወበጽሐ ኀበ ብሉየ መዋዕል ወተውህበ ሎቱ መንግሥት ወምኵናን መንግሥቱኒ መንግሥት ዘለኵሉ ዓለም ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ እንዲል ። ታሪክ ዘፍ ፳፬ ፣ ፩ ። እግዚአብሔር ሥራውን አለ ምክንያት አይሠራውም ለአብርሃም ኢያውብር የሚባል ዘመድ ሎሌ ነበረው በሚሞትበት ጊዜ አስጠርቶ ልጄን ይስሐቅን ሶርያ ወርደህ ከዘመዶቼ ወገን አጋባው እንጂ ከአዋልደ ከነዓን እንዳታጋባው ማል እጅን ጽፋ ጉልበቱን ምታ አለው እጅን ጽፋ ማለቱ የሰጠኸኝ አይባረክልኝ በል ሲል ነው ። ጉልበቱን ምታ ማለቱ የወለድኩት አይባረክልኝ በል ሲል ነው ። እሱም ጠንቅቆ ይምላል ያች የማመጣት ብላቴና አልመጣም ያለች እንደሆን ወደ ነበርክበት እሱን ይዤው ልሒድን አለው ዑቅ ኢታግብእ ለወልድየሰ ባሕቱ ዘሐፀነኒ ወሴሰየኒ ይፌኑ ለከ መልአኮ እግዚአብሔር መንገድህን ያቃናልሀል አምጥተህ አጋባው እንጂ እሱንስ አትውሰደው አለው ።

ከቃው መልከሙን መርጦ ዐሥር ግመል ጭኖ ሄደ ወደማታ ከውሃ ዳር አርፎ ያወጣ ያወርድ ጀመር ውሃ ከሚቀዱት ሴቶች ከጌታዬ ዘመዶች ወገን ሁና መልከ ከደም ግብት አስተባብራ የያዘች ሕፃን ሁና ውሃ አጠጭኝ ብያት አጠጥታኝ ለግመሎቼም የምታጠጣልኝ ሁና ኪያሃ አስተዳሉከ ለገብርከ ይስሐቅ ባልኩ ነበር እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ወእምቅድመ ያኅልቅ ተናግሮ ይላል ሐልዮ ሲል ነው ይህን ተናግሮ ሳይፈጽም ርብቃ ባጭር ታጥቃ ማድጋ ነጥቃ መጣች ። ቀድታ በምትሄድበት ጊዜ ወሃ አጠጭኝ አላት ቀድታ አጠጣችው ለግመሎችህ ላጠጣልህን አለችው ይሁን አለ እየቀዳች አጠጣችለት አስተያየቷን አረጋገጧን ይመለከታል የማን ልጅ አላት ። ሚልካ ለናኮር የወለደችለት የባቱኤል ልጅ ነኝ አለችው ። ከቤትሽ ማደርያ አይገኝምን አላት ምንታጥቶ አንተ የምትበላው ዳቦ የምትጠጣው ጠጅ የምትተኛበት አልጋው ለግመሎችህ ጋጡ ገፈራው ተርፏል አለችው ።

ወእምዝ ረወዩ አግማሊሁ ነሥአ ኢያውብር አዕኑገ ዘወርቅ እንዲል ፣ ያሥር ወቄት ለሁለቱ እጆቹዋ አምባር የሁለት ወቄት ለሁለቱ ጆሮቹዋ ጉትቻ አለጊጦ ሰደዳት ላባ የሚባል ስሱ ወንድም አላት ማን ሰጠሽ አላት እንዲህ ያለ ሰው አስጊጦ ሰደደኝ አለችው ። እንደሷ የሚያገኝ መስሎት ሄደ ።

አንተን ያህል ሰው ከዚህ ምን አኑሮሃል አንተ የምትበላው ዳቦ የምትጠጣው ጠጅ የምትተኛበት አልጋው ምንጣፉ ለግመሎችህ ጋጡ ገፈራው ተርፎ ከቤት ገብተህ እህል ቅምሰህ ውሃ ጠጥተህ እታር ፍምን ብሎ ይዞት ሄደ ከገባ በኋላ እግርህን ታጥበህ ዕረፍ አሉት ። ጌታዬ የላከኝን ሳልናገር ሌላ ሥራ አልሠራም አለ ።

የንጉሥ መልክተኛ የታዘዘውን ሳያደርግ ሌላ ሥራ እንዳይሠራ ፀል ተናገር አሉት ፣ እሱም ጌታዬ አብርሃምን አልቆ አክብሮታል ከረጀ በኋላ የወለደው የሚወደው ልጅ አለው ከአዋልደ ሶርያ እንጂ ከአዋልደ ከነዓን እንዳታገባው ብሎ አምሎኛል ገንዘብ ይገዬ መጥቼ ከውሀ ዳር ዐርፌ ሳወጣ ሳወርድ ይህች ብላቴና መጥታ እንደምታዩት አስጊጬ ሰደድኳት ለጌታዬ ልጅ ሚስት ልትሆን ስጡኝ እናንተም ገንዘባችሁን ተቀበሉኝ አላቸው ።

እነሱም ንሕነሰ ኢንክል ተናገር ኢ ሠናየ ወኢ እኩየ አሉት ። ነገር ወስኑልኝ ቈረጡልኝ እንጂ እኔማ ቀኝስ ግራስ ብል ምን አጥቼ አለ ። አማጭ ለል ማዱ የበቅሎ ክበድ የሐር ገመድ አለኝ ይላልና ይሁን ተቀመጥ አሉት አደረ ። ቢነጋ አስናብቱኝ ገንዘባችሁን ተቀበሉኝ ልጅቷንም ስጡኝ አለ ። ዐሥር ቀን ትረፍ አሉት ኢታስተድኅሩኒ እግዚአብሔር ነገሬን አቅንቶልኝ ሳለ አታስናክሉኝ አላቸው ባይሆን እሷን እንጠይቃት ብለው ጠየቋት እሄዳለሁ አለች ገንዘቡን ሰጥቶ ይዞ መጣ ይስሐቅ ወንበዴ እንዳይጣላቸው ብሎ መንገድ አላፊ መስሎ ይሰልላል አራምዳ አይታ ያማነ ው አለችው የም ትሄጅለት የጌታዩ ልጅ ነው አላት ።

ተራ ልብስ ለብሳ ነበርና አውርዱኝ ብላ አጊጣ ቆየች ይዟቸው ሂዷል ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው አብር ሃም የእግዚአብሔር አብ ኢየውብር የቅዱስ ገብር ኤል ይስሐቅ የመለኮት ርብቃ የትስብእት ፣ ዐሥሩ ወቄት ያሥሩ ቃላት ሁለቱ ወቄት የፍቅረ ቢጽና የፍቅረ እግዚአብሔር አንድም ፪ቱ ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ ያለው ፣ ዐሥሩ አፎኑ ከመ ዝኑ እንጋ ካለው ጀምሮ ወአልቦ ማኅለቅት ስመ ንግሥቱ እስካለው ዓሥር ይሆናል የዚህ ምሳሌ ። ሳድስ ወርኅ ያለውም በስድስተኛው ሺህ ቢል ነው እንኳን በወር በዕለት ይመስለዋል ። በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቀ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ እንዲል ።

፴፬ ትቤሎ ማርያም ለመልአክ እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ ።

፴፬ ወንድ ሳላውቅ መፅነስ መውለድ እንደ ምን ይሆንልኛል ፣ እምአይቴ ረከብኩ ዘከመዝ ብሥራተ ዘእንበለ ምት እምድንግል ፅንሰተ ወዘእንበለ ዘርእ እምድር ዕትወተ እንዲል ፣ ምድር ያለ ዘርዕ ታፈራ ዘንድ ሴት ያለወንድ ትፀንስ ዘንድ እንዲህ ያለ የምሥራች ከማን አገኘኸው አለችው እንዲህ ማለቷ ነገሩን ሽታው አይደለም ጥንቱን እንደምን ይሆንልኛል ነገሩን አላደርገውም ስትል ነው እንጂ ዘንተ ትቤ ድንግል በእንተ ዘኢዓርገ ሕሊና ዕጓለ እመሕያው ውስተ ልባ እንዲል ።

፴፭ አውሥአ መልአክ
፴፭ መልአኩም መሰሰ
ወይቤላ መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ። ያንችማ ፅንስ መቼ እንደ ሌሎች ሴቶች ፅንስ ነዋ መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል ።
ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ።
ኃይለ ልዑል ወልድ ሥጋሽን ይለብሳል አንድም መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል ኃይለ ልዑል ወልድ ከሦስቱ ግብራት ይከለክልሻል ወውእቱኒ ንጹሕ እምሠለስቱ ግብራት እለ ሥሩዓት በዕጓለ እመሕያው እንዲል ።
ወዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ።
ካንች የሚወለደውም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለው ከሚመስገኑ ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ነው ።
ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ።
የልዑል እግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ይባላል ።

፴፮ ወናሁ ኤልሳቤጥኒ እንተ ንምአዝማድኪ ይእቲኒ ፀንሰት ወረከበት ወልደ በልሀቃቲሃ ወበ ርስአቲሃ ።

፴፮ ከዘመዶችሽ ወገን የምትሆን ኤልሳቤጥ ስንኳ በፍጹም እርጅናዋ ልጅ አግኝታ ፀንሳለች ። ሐተታ ፣ ኤልሳቤጥ ስንኳ ማለቱ ስለ ምን ነው ቢሉ እመቤታችን ምንም በድንግልና ቢሆን ሙቀት ልምላሜ አልተለያትም ። ኤልሳቤጥ ግን ምንም በዘር በሩካቤ ቢሆን ሙቀት ልምላሜ ተለይቷት ነበርና ። ይህማ ሙቀት ልምላሜ ሳለ በድንድልና እንዲወልዱ ፣ ሙቀት ልምላሜ ከተለየ በኋላ በዘር በሩካቤ እንዲወልዱ የሚያደርግ እሱ አይደለምን ብሎ መጽሐፍ ያለበትን ማፅናት ልማድ ነውና እን ዲህ አለ ። አንድም ከዘመዶችሽ ወገን የምትሆን ኤልሳ ቤጥ በል ።
ወናሁ ሣድስ ዝንቱ ወርኅ ለእንተ ይብልዋ መካን ።
መካን ለሚሏት ለኤልሳቤጥ ከፀነሰች እነሆ ይህ ወር ስድስተኛ ነው ።

፴፯ እስመ አልቦ ነገር ዘይስእኖ ለእግዚአ ብሔር ።

፴፯ ሙቀት ልምላሜ ሳለ እንበለ ዘርእ እን ዲወልዱ ቢያደርግ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላእሌኪ ላለው ። አንድም ሙቀት ልምላሜ ከተለየ በኋላ በዘር በሩ ካቤ እንዲወልዱ ቢያደርግ የሚሳነው ነገር የለምና ወናሁ ኤልሳቤጥኒ ላለው ።

፴፰ ትቤሎ ማርያም ለመልአክ ነየ አመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ።

፴፰ እንዲህ ባላት ጊዜ እመቤታችን ስመል አኩ የእግዚአብሔር ገረዱ እነሆ አለሁ እንዳልክ ይሁንልኝ አለች ። በዚህ ጊዜ ቃሏን ምክንያት አድ ርጎ አካላዊ ቃል በማኅፀኑዋ ተቀርጹዋል ። ሐተታ እንደ እደ ፀሐፊ ሠልጣነ እግዚአብሔር እንደ ብርአ ፀሐፊ የመንፈስ ቅዱስ በቀንዱ ያለ ቀለም የሌሎች ሴቶች ባሕርይ በብርዑ ያለ ቀለም የእመቤታችን ባሕርይ ምሳሌ አስትንፋሱ የመንፈስ ቅዱስ አልወርድ ቢለው እፍ እያለ ያወርደዋል ፣ የፈጠረ የከፈለ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነውና ምሥጢሩ የአካላዊ ቃል ቀለሙ የትስብዕት ረቂቅ

ምሥጢር ከልቡና ሳይለይ በቀለም ገዝፎ እንዲታይ ፣ ረቂቅ አካላዊ ቃልም ከአብ አንድነት ሳይለይ በሥጋ ገዝፎ ታይቷል ። አንድም ወሀየንተ አድዘዝየ ያግኅድ ከመ እግዝእትን ማርያም ይእቲ ይሳል ብሎ እንደ እደ ጸሐፊ ይኩነኒ ያለችው የቃሏ ምሳሌ ሖረ ወኀሰፈ እምኃቤሃ መልአክ ።
የቦታ ላስው እሷ ካለችበት ሄደ ባሕርይዋን መስለላት ላለው ተሰወራት ።

በእንተ ብጽሐት ኀበ ኤልሳቤጥ

፴፱ ወተንሥአት ማርያም ፍጡነ በውእቱ መዋዕል ወሖረት ደወለ ዓይነ ከርም ።

፴፱ እመቤታችን በዚያ ወራት ፈጥና ደጋ ደጋውን ሄደች አንድም ጮቄ ጮቄውን የክረምት ግብር ባለበት ጉም በሚሰብበት ዝናም በሚዘንብበት ለተክል የሚያጡት ወሀ በሚሄድበት በስርጥ ጉዳና ሄደች ። ሐተታ ስለ ሦስት ነገር ትሄዳለች ኤልሳቤጥ ፀ ሰች ብሏታልና የኤልሳቤጥን ፅንስ ለመረዳት ዘካርያስ ታመመ ብላዋታልና ለመጠየቅ ፣ ምስክር ሦስት ለማድረግ መልአኩ መስከሯል ፣ ዮሐንስ በማኅፀን የሚሰግድ ነው ፣ ኤልሳቤጥም እሙ ለእግዚእየ የምትል ናትና ።

ወበጽሐት ሀገረ ዳዊት ዘይሁዳ ።
ይሁዳ ከሚባል አገር ደረሰች ።

፵ ወቦእት ቤተ ዘካርያስ ወአምኃታ ለኤልሳቤጥ

፵ ከዘካርያስ ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን እንዴት ነሽ አለቻት ወሶበ ሰምዓት ኤልሳቤጥ ቃላ ለማርያም እንዘ ትትኣምኃ ኦንፈርዓፀ እጓል በውስተ ከርሣ እመቤታችን እንዴት ነሽ ስትላት ኤልሳቤጥ በስማች ጊዜ በማኅፀኑዋ ያለ ብላቴና ሰገደ ሐተታ ፣ ሐዋርያት በሲኖዶስ ሰገደ ብለውታል ። ያሬድም ሰገደ ብሎታል ።

፵፩ ወመልአ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኤልሳቤጥ

፵፩ በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ አደረባት ቀለ ይቷትን ያውቃል ሥራ አሰራት ሲል ነው ።

፵፪ ፤ ወከልሐት በዓቢይ ቃል ።

፵፪ ቃሏን ከፍ አድርጋ ኦሰምታ ተናገረች ። ወትቤ ቡርክት አንቲ እምአንስት ።
ከሴቶች ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌላብሽ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እያማለድሽ የምታሰጭ ነሽ ።
ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ ።
የማኅፀንሽም ፍሬ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚያድል ነው ።

፵፫ ወምንትኑ አነ ከመ ትምጽኢ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ ።

፵፫ የጌታዬ እናቱ እመቤቴ ወደኔ ትመጭ ዘንድ እኔ ምንድነኝ ፣ ስልማዱ ገረድ ወደ እመቤቷ ትሄዳለች እንጂ እመቤት ወደ ገረዱዋ ትመጣለችን አለቻት ።

፵፬ እስመ ናሁ ሶበ ሰማዕኩ እንዘ ትትአምኀኒ አንፈርዓጸ እጓል በውስተ ከርሥየ በፍሥሐ ወበኃሤት ።

፵፬ እንዴት ነሽ ስትዪኝ በሰማሁ ጊዜ በማኅፀኔ ያለ ብላቴና ደስ ብሎት ሰግዷልና ።

፵፭ ወብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃለ ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር ።

፵፭ ከእግዚአብሔር አግኝተው የነገሩሽን ነገር እንዲደረግ የምታምኚ አንድም ከመ ይከውን ቃል ከእግዚአብሔር አግኝተው የነገሩሽ ነገር እንዲደረግ የምታምኝ አንቺ ንፅሕት ክብርት ነሽ ። ሐተታ መጽሐፍ ስም ካልጠራ ማብዛት ልማዱ ነውና የነገራት አንድ ገብርኤል ሲሆን አብዝታ ተናገረች በተአምኖ አመ ንነርዎ ለኖኅ በእንተ ዘኢያስተርኢ ግብር ዘኀቡዕ ፈርሃ እንዲል ፣ የነገረው አንድ ሱርያል ሲሆን ።

፵፮ ወትቤ ማርያም ታዓብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ።

፵፮ እመቤታችን ስውነቴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች ።

፵፯ ወትትኃሠይ መንፈስየ በአምላኪየ ወመድኃንየ ።

፵፯ ልቡናዬም በፈጣሪዩ በመድኃኒቴ እምና ደስ ይላታል አለች ። ሐተታ ፣ ከምን አድኑዋታል ቢሉ ከንዴተ ህላዌ ከልማደ አንስት ።
እሸመ ርእየ ሕማማ ለአመቱ የገረዱን የሔዋንን መከራዋን አይቷልና ። አንድም ትሕትናዋን በእግረ አጋንንት መረገጧን አይቷልና ኦንድም የኔን የገረዱን ትሕትናዩን ኦይቷልና ። ሐተታ ይህስ እንደምን ነው ቢሉ መጽሐፈ ኢሳይያስ ስትመላከት ። ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ከሚለው አንቀጽ ብትደርስ ድንግልና እያላት ምነው እኔ በሆንኩ ኦላለችም እንዲህ ካለችዩቱስ ከጊዜዋ ደርሼ ወጥቼ ወርጄ ኦገልግያት ብላ ተመኝታለች እንጂ ኃዘኔን ሰምቷልና ምን እያለች ታዝን ነበረ ቢሉ የተቆጥረጦ ሱባኤ ደረሰ የተነገረው ትንቢት ቀረ እያለች ታዝን ነበረ ።

፵፰ ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ ።

፵፰ ከንግዲህስ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ። ሐተታ ባንድ መልአክና ባንዲት ባልቴት ቃል ብቻ ተመሰግኝ እቀራለሁን ትውልደ ሴም ትውልደ ካም ትውልደ ያፌት ሁሉ ያመሰግኑኛል ስትል እንዲህ አለች ዞሉ አለ ከዚህ የወጣ ትውልድ የለምና ። አንድም ፍጥረት ሲል ነው ። አራት ዘልደት እንዲል ፍጥረት ሁሉ ያመሰግኑኛል።

፵፱ እስመ ገብረ ሊተ ኃይለ ዓቢያተ ።
፵፱ ደግ ነገር ሥራ ሠርቶልኛልና
ሐተታ ፤ አብ ቢሉ ልጁን ወልድ ቢሉ አካሉን በኀቱም ድንግልና ፀንሼ በኀቱም ድንግልና እንድወልደው አድርጎኛልና
ወቅዱስ ስሙ ።
ይህን ያደረገልኝ ስሙ ልዩ ነው ። ሐተታ አብ ይባላል እንጂ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይባልም ወልድ ይባላል እንጂ አብ መንፈስቅዱስ አይባልም፤ መንፈስ ቅዱስ ይባላል እንጂ አብ ወልድ አይባልም

፶ ወሣህሉኒ ለትውልደ ትውልድ
፶ ይቅርታውም ለልጅ ልጅ ነው ለእለ ይፈርህዎ ።
ያው ግን ለሚያመልኩት ለሚፈሩት ፤ ሐተታ አባቷ ዳዊት ሣህሉሰ ለእግዚአብሔር እምዓለም ወእስከ ለዓለም ዲበ እለ ይፈርህዎ ብሎ ነበርና ከዚያ አያይዛ እንዲህ አለች ።

፶፩ ወገብረ ኃይለ በመዝራዕቱ ። ኢሳ. ፶፩ ፥ ፱።
፶፩ አብ ቢሉ በልጁ ። ወልድ ቢሉ በሥልጣኑ ደጋግ ተአምራት አደረገ ።
ወዘረዎሙ ለእለ ያዓብዩ ሕሊና ልቦሙ ።
ትዕቢተኞች ጸሐፍት ፈሪሳውያንን አጋንንትን በተናቸው ።

፶፪ ወነሠቶሙ ለኃያላን እመናብርቲሆሙ ።
፶፪ ኃያላን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ከሹመታቸው ሽራቸው ከልዕልናቸው አዋረዳቸው አንድም ኃያላን አጋንንትን ከማደሪያቸው ከሰው ለያቸው
አዕበዮሙ ለትሑታን ።
ትሑታን ሐዋርያትን ዐሥራት በኵራት ቀዳምያት ሰጥቶ ትሑታን ነፍሳትን ልዕልና ነፍስ ሰጥቶ አከበራቸው ።
፶፫ ወአጽገቦሙ እምበረከቱ ለርሁባን ። ፩ ነገ ፪ ፭ ። መዝ. ፴፫ ፥ ፲
፶፫ ዓሣ ሶጋሪ ልብደ ሠሪ የነበሩ ርሁባን ሐዋርያትን ዐሥራት በኵራት ቀዳምያት ሰጥቶ አጸገባቸው ርሁባን ነፍሳትን ሥጋውን ደሙን ልጅነትን ሰጥቶ ደስ አሰኛቸው ።
ወፈነዎሙ ዕራቆሙ ለብዑላን ዐሥራት በኵራት ቀዳምያት ተቀብለው ይኖሩ የነበሩ ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ባዶ እጃቸውን ሰደዳቸው ብዑላን አጋንንትን ባዷቸውን ሰደዳቸው ።

፶፬ ወተወክፎ ለእስራኤል ቍልዔሁ ።
፶፬ እንዲህ አድርጎም እሥራኤል ዘሥጋን ተዋሕዶ ኀበ ያዕቆብ ኀድረ ወኀበ እስራኤል ተዋረሰ እንዲል ።

፶፭ ወተዘከረ ሣህሎ ዘይቤሎሙ ለአበዊነ ለአብርሃም ወለዘርኡ እስከ ለዓለም ። ዘፍ ፲፯ ፥ ፲ መዝ ፻፴፩ ፥ ፲፩ ። ኢሳ. ፵፩ ፥ ፰ ።

፶፭ ላባቶቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የነገራቸውን ይቅርታውን እስከ ዘለዓለም አሰበ።
፶፮ ወነበረት ማርያም ኀቤሃ መጠነ ሠለስቱ አውራኅ ።
፶፮ እመቤታችን ሦስት ወር ከኤልሳቤጥ ዘንድ ኖረች ።
ወእምድኅሬሁ አተወት ቤታ ከሦስት ወር በኋላ ወደ ቤቷ ተመለሰች ።

በእንተ ልደተ ዮሐንስ መጥምቅ ።

፶፯ ወበጽሐ ዕርኃ ለኤልሳቤጥ ከመ ትለድ፤
፶፯ ኤልሳቤጥ ልጅ የምትወልድበት ጊዜው ደረሰ ፤ ሐተታ ፤ ከዚያ ኑራ ቢሆን የመለኮት እናት ተልእኮ ባገኘች ነበርና ፤ ይህማ እንዳይሆን ጌታ የመጣው ለትሕትና ነው እንጅ ለልዕልና ነውን ብሎ እመቤታችን ነማናዊት ቤተ መቅደስ ነችና ኅርስ ርስሐት እንዳያገኛት ።
ወወለደት ወልደ ።
ወንድ ልጅ ወለደች ።
፶፰ ወሶበ ሰምዑ አዝማዲሃ ወአግዋሪሃ ከመ አዕበየ እግዚአብሔር ሣህሎ ላዕሌሃ ።
፶፰ ጐረቤቶቿና ዘመዶቿ እግዚአብሔር ይቅርታውን እንዳበዛላት ማለት ልጅ እንደሰጣት በሰሙ ጊዜ ።
ተፈሥሑ ላቲ ።
በሷ ደስ አላቸው ። አንድም ምስሌሃ ከሷ ጋራ እንደሷ ደስ አላቸው ። ሐተታ ፤ በትምህርቱ በትንቢቱ ደስ ያሰኛቸዋልና ።
፶፱ ወእምዝ እመ ሰሙን ዕለት መጽኡ ይግዝርዎ ለሕፃን ።
፶፱ ከዚህ በኋላ በስምንተኛው ቀን ሊገዝሩት መጡ የሌዊ ካህናት ልጅ ነውና አክብረው ሊገዝሩት መጡ አለ ። ሌሎቹን ግን እያመጡላቸው ይገዝሩ ነበር ። ሐተታ ወይም ዝቅ ብሎ ቢሆን ሰውነቱ ልሕሉሕ ይሆናል ወይም ከፍ ብሎ ቢሆን ሰውነቱ ያጠናል ይሰማዋልና አማካይ ቀን ሽተው ። ምስጢሩ ግን የሰምንቱ ብሔረ አሪት ምግብና ሲፈጸም ግዝረተ ነፍስ የሰምንቱ ሺህ ምግብና ሲፈጸም ግዝረተ ሥጋ ሶሰው እንዲሰጠው ለማጠየቅ
ወይሰምይዎ በስመ አቡሁ ዘካርያስ ።
ባባቱ ስም ዘካርያስ ይሉት ዘንድ ። ሐተታ እኛ ዛሬ ለወንድ ልጅ ባርባ ቀን ለሴት ልጅ በሰማንያ

ቀን በዕለተ ጥምቀት ስም እንድናወጣ እነሱም በዕለተ ግዝረት ስም ያወጡ ነበርና ።

፷ ወአውሥአት እሙ
፷ እናቱም መለሰች
ወትቤ አልቦ ። አይሆንም
አላ ዮሐንስ ይሰመይ ስሙ ።
ስሙ ዮሐንስ ይባል እንጂ አለች ።

፷፩ ወይቤልዋ አልቦ እምአዝማድኪ ዘከማሁ ስሙ ።

፷፩ ከዘመዶችሽ ወገን እንዲህ ያለ ስም የለ እንደምን ይሆናል አሏት ።

፷፪ ወቀጸብዎ ለአቡሁ
፷፪ አባቱን ጠቀሱት
ወይቤልዎ መኑ ትፈቅድ ይሰምይዎ ።
ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ ነውና ማን ቢሉት ትወዳለህ አሉት ።

፷፫ ወስአለ ለውሐ ። ሉቃ ፩ ፲፫
፷፫ ዓይኑ ዓ ነው ያሉ እንደሆን ጻፈ አልፋው አ ነው ያሉ እንደሆን ብር ቀርጻችሁ ብራና ደምፃችሁ ቀለም በጥብጣችሁ ስጡኝ ብሎ ለመነ ።

ወጸሐፈ እንዘ ይብል ዮሐንስ ይሰመይ ስሙ ስሙ ዮሐንስ ይባል ብሎ ጻፈ ።

ዮሐንስ ይሰመይ ስምንቱን ቀለም ጽፎ ከዚህ በኋላ ተናግሯል ሰው ሁሉ የስምንቱ ብሔረ አሪት የስምንቱ ሺህ ምግብና ሲፈጸም በልሳነ ነፍስ እንዲናገር ያጠይቃል አንድም ዮሐንስ ይሰመይ ስሙ ብሎ ፲ን ጽፎ ተናግሯል ያሥሩ ቃላት ምግብና ሲፈጸም ሰው ሁሉ በልሳነ ነፍስ እንዲናገር ያጠይቃል ።

፷፬ ወአንከሩ ኵሎሙ ።
፷፬ ሁሉም አደነቁ ።
ወከሠተ አፉሁ ወነበበ ።
አንደበቱ ረቶ ተናገረ ።
ወባረኮ ለእግዚአብሔር ።
እሱም እግዚአብሔርን አመሰገነ ። ሐተታ ከዚህ ጊዜ ያደረሰኸኝ ብሎ ።
፷፭ ወኮነ ፍርሃት ላዕለ ኵሉ ሰብእ ዘውእቱ ብሔር ወላዕለ ኵሉ ደወለ ይሁዳ ።
፷፭ በይሁዳና በዚያ አገር ባሉ ሰዎች ሁሉ የአንክሮ ፍርሃት አደረባቸው ።
ወተናገርዎ ለዝንቱ ነገር ላዕለ ኵሉ ደወለ ይሁዳ ።
በይሁዳ አውራጃ ሁሉ ይህን ነገር ተጫወቱት ።
፷፮ ወዓቀብዎ በልቦሙ እለ ሰምዕዎ
፷፮ የሰሙት ሁሉ በልቡናቸው አስተዋሉት ።
ወእሙሰ ተዓቅብ ዘንተ ኵሎ ነገረ ወትወድዮ ውስተ ልባ እንዲል ።
ወይቤሉ ምንትኑ ይከውን እምዝንቱ ሕፃን ።
ከዚህ ሕፃን የተነሣ ምን ይሆን እንድም ይህ ብላቴና እንደምን ያለ ይሆን እንደ ኖኅ አበ አንጋድ እንደ ሙሴ ጠላት ይገድል ባሕር ይከፍል ደመና ይጋርድ መና ያወርድ እንደ ኢያሱ በረድ ያዘንም ፀሐይ ያቆም እንደ ጌዴዎን ጸምር ይዘረጋ ጠል ያወርድ እንደ ኤልያስ ሰማይ ይለጕም እሳት ያዘንም ይሆን አሉ ።
እስመ እዴ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ።
የእግዚአብሔር ኃይል አድሮበታልና ።

፷፯ ወመልአ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ዘካርያስ አቡሁ ።

፷፯ በዘካርያስ መንፈስ ቅዱስ አደረበት ። ሐተታ ተለይቶትን ያውቃል ቢሉ ሥራ አሠራው ሲል ነው ።
ተንበየ ወይቤ ። ተንበየ ብሎ አንድ አርእስት ይቤ ብሎ ፪ት አርእስት ተናገረ ፡ለሁለቱም ያመጣል ፤

፷፰ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘተሣሀሰነ ወገብረ መድኃኒተ ለሕዝበ ዚአሁ መዝ ፻፲ ፡ ፱ ።

፷፰ ይቅር ያለን ለወገኖቹ ደኅንነትን ያደረገልን የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብሎ ተናገረ ።

፷፱ አንሥአ ለነ ቀርነ መድኃኒትነ እምቤተ ዳዊት ገብሩ ። መዝ ፡ ፻፴፩ ፡ ፲፯ ።

፷፱ ከባለሟሉ ከዳዊት ወገን የምንድንበት ክርስቶስን ያሥነሣልን ። ሐተታ ፤ ቀርን ጸለው እንስሳት በቀንዳቸው ድል እንዲያደርጉ ምእመናንም በሱ አጋንንትን መናፍቃንን ድል ይነሡበታልና ብከ ንወግዖሙ ለኵሎሙ ፀርነ እንዲል አንድም አራት ሽቱ አምስተኛ በዘይት አጣፍጠው በቀንድ አድርገው ያኖራሉ መንግሥት የሚገባቸው ከቤተ ይሁዳ የተወለዱ ቀኝ አካላቸውን ተቀብተው መንግሥትን ። ክህነት የሚገባቸው ከቤተ ሌዊ የተወለዱ ቀኝ አካላቸውን ተቀብተው ክህነትን እጅ ያየርጋሉ እሱም እንደ አራት ሽቱ አራቱን ባሕርያተ ሥጋ እንደ አምስተኛ ዘይት ባሕርየ ነፍስን ነሥቶ ክህነትን መንግሥትን ለራሱ ገንዘብ አድርጎ ለምእመናን የሚያድል ሁኗልና

፸ በከመ ነበበ በአፈ ነቢያቲሁ ቅዱሳን እለ እምዓለም ኤር ፳፫ ፡ ፮ ።

፸ እለ እምሰብእ እለ እምጥንት ሲል ነው ከሰው ወገን በሚሆኑ ከጥንት በነበሩ ንፁዳን ፤ ከቡራን በሚሆኑ በነቢያት አድሮ እንደተናገረ ።

፸፩ ከመ ያድኅነነ እምእደ ፀርነ ።
፸፩ ከጠላቶቻችን እጅ ያድነን ዘንድ ።

ወእምእደ ኵሎሙ እለ ይጸልኡነ ።
ከሚጠሉንም ሁሉ እጅ ማለት ከእኩያት ፍትወታት ኃጣውእ ያድነን ዘንድ ።ሐተታ የሚያጣሉን ስለሆነ ይጸልዑነ አለ ።

፸፪ ከመ ይግበር ማህሉ ምስለ አበዊነ ።
፸፪ ላባቶቻችን ያደረገውን ላባቶቻችን እንዳደረገላቸው ካባቶቻችን ጋራ ይቅርታውን ያደርግ ዘንድ ።
ወከመ ይዘከር ኪዳኖ ቅዱስ ዕኑዕ መሐላውን ያስብ ዘንድ

፸፫ መሐላሁ ዘመሐለ ለአብርሃም አቡነ ።
ዘፍ ፳፪፥፲፮ ፡ ኤር ፴፩፥፴፫ ፡ ዕብ ፮፥፲፫ ።

፸፫ መሐላውም ላባታችን ለአብርሃም የማለው ነው ።

፸፬ ከመ የሀበነ በዘኢንፈርህ እምእደ ፀርነ።
፸፬ በጠላቶቻችን በአጋንንት እጅ የተወረወረው ጦር የተጣለው ጦር ያገኘናል ብለን በማንፈራ ገንዘብ የማንፈራበትን ሥጋውን ደሙን ልጅነትን ይሰጠን ዘንድ ።

፸፭ ያድኅነነ ናምልኮ በጽድቅ ወበርትዕ ።
፸፭ በጽድቀ አሚን ጸንተን በንጽሐ ጠባይዕ ሁነን እናምነው ዘንድ ። አንድም በወንጌል በኦሪት ሁነን እናምልከው ያድነን ።
በቅድሜሁ ።
እሉ ባለበት ዘመን ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ።
ወበኵሉ መዋዕሊነ ።
እኛ ባለንበትም ዘመን ሁሉ አንድም በቅድሜሁ በኵሉ መዋዕሊነ ፤እሱ ባወቀው ባለንበት ዘመን ሁሉ እምልከነው ያድነን ዘንድ ።

፸፮ ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ ።
ሚል ፬፥፭ ሉቃ ፩፥፲፯ ።

፸፮ ይቤ ለሰው ጨርሶ ተነበየ ላለው አመጣ አንተም ብላቴና ልዑል እግዚአብሔር የሾመህ መምህር ትባላለህ ።
እስመ ተሐውር ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ትጹሕ ፍኖቶ መንገድ ልትጸርግ በእግዚአብሔር ፊት ትሔዳለህ ማለት ሰውን ከኃጢአት ከጣዖት ትለይ ዘንድ መንፈቅ ተቀድመህ ታስተምራለህና ።

፸፯ ከመ ተሀቦሙ ያእምሩ መድኃኒቶሙ ።
፸፯ ተሀቦሙ መድኃኒቶሙ ያእምሩ መድኃኒቶሙ ብለሕ ግጠም መድኃኒታቸው ክርስቶስን ነዋበግዑ ብለህ ትዳርጋቸው ዘንድ ። ያእምሩ ሊያውቁ አንድም መድኃኒታቸው ክርስቶስን ሊያውቁ ታስተምራቸው ዘንድ ።

፸፰ በዘይትኃደግ ሎሙ ኃጢአቶሙ በምህሉ ወበምሕረቱ ለአምላክነ ለዘሐወፀነ እምአርያም ዘካ ፫፥፱ ፡ ሚል ፬፥፪ ።

፸፰ ለና ለ አንድ ወገን ከአርያም ወርዶ በኃበኛን በፈጣሪያችን ይቅርታና ቸርነት ኃጢአታቸውን በሚስረይላቸው ገንዘብ ይስረይላቸው ዘንድ፤

፸፱ ወሠረቀ ከመ ያርዕዮሙ ብርሃኖ ለእለ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ።

፸፱ በድንቁርና በቀቢጸ ተስፋ ላሉ ዕውቀትን ይገልጽ ዘንድ ተወለደ ።
ከመ ያርትዕ እገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም ።
እግረ ሕሊናችንን ወደወንጌል ጎዳና ያቃናልን ዘንድ

፹ ወልኅቀ ሕፃን ።
ብላቴናው አደገ ።

፹ ወጸንዐ በመንፈስ ቅዱስ ።
በመንፈስ ቅዱስ ጸና ። ሐተታ ልጅ የሚያሳድግ ብቻ ጣቢታ አይደለም ኃይል አልኀቂተ ኵሉ አለችና ጸንዓ በመንፈስ ቅዱስ አለ ።
ወነበረ ኃቅለ እስከ አመ ያገይሥዎ ኀበእሥራኤል ምክራቸው አስተምራቸው ብ/ው ሥላሴ ወደ እሥራኤል በመምህርነት እስኪያግልጹት ድረስ አንድም እስራኤል ምከረን አስተምረን ብለው በመምሕርነት እስኪግልጹት ድረስ በበረሃ ኖረ ። አንድም እስከ አመ ያስተርኢ ሎሙ ለእሥራኤል ይላል እብነትለእሥራኤል በመምህርነት እስኪ ገለጽ ድረስ በበረሃ ኖረ ።

በእንተ ልደተ ኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወኮነ በውእቱ መዋዕል ወፅአ ትእዛዝ እምኀበ አውግሥጦስ ቄሣር ከመ ይጸሐፍ ኵሉ ዓለም።

፪ ኮነ ያለውን ወጽአ ብሎ አመጣው ሰው ሁሉ ከግብር ይቈጠር ዘንድ በዚያ ወራት ከአውግሥጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣ ጸሐፊዮ ለውእቱ ብእሲ ከመ ዘሞተ እንዲል ። ሐተታ ፤ እውግሥጦስ ማለት ሠጣጪ ክርሥ ቄሣር ማለት ጸዳል ማለት ነው ይህስ እንዳይሆን ጌታ በዘመኑ ተወደል ብሎ እውግሥጦስ ማለት ፀዳል ማለት ነው ። ቄሣር ማለት ሠጣጪ ክርሥ ማለት ነው ። ታሪክ የሮም ንጉሥ ካንድ ጕልማሳ ሚስት ያለ ፈቃዷ ደረሰባት ባሏን ትወድ ነበርና ያለ ፈቃዴ ደረሰብኝ ብላ ታንቃ ሞተች ፤ ወንድሞቹዋ እኅታችን የሞተች እንጂ በሱ ምክንያት ነው ብለው ከቤተ ጣዖት ገብቶ ሲወጣ ሸምቀው ገደሉት ኋላ ሕዝቡ እሱስ እኳ የሞቱ አንድ ሰው ብናሠለጥን አይደለም ብለው ነገር የሚወስኑላቸው መቶ ሃያ ባውላ ሹመዋል ከመቶ ሃያው ባውላ ያንዱ ባውላ ሚስት ፀንሳ ሳለች በምትወልድበት ጊዜ ሞተች ገንዘው እንቀብራለን ሲሉ ፅንስ ተንቀሳቀሰ ሕያውን ከምውት ጋር እንቀብራለን ብለው ሆዷን ቀደው አወጡት

አደገ ኃያል ምሑረ ጸብእ ሆነ እኒህን ሁሉ አጥፍቶ ነግሢል እንድም ኃይለኛ ጠላች ተነሥቶባቸው አጥፋልንና እናነግሥሃስን ብለውት አጥፍቶላቸው አንግሠውታል ። ከባውላው ወገን ስለ ተወለደ ብልዮስ ቄሣር ብለውታል ፣ ብልዮስ ቄሣር ጋብዮስ ቄሣርን ጋብዮስ ቄሣር አውግሥጦስ ቄሣርን ፣ ይወልዳል ይህ ሦስተኛ ቄሣር ነው ።

፪ ወውእቱ ጸሐፍ ቀዳሚ ።

፪ ይህ ቍጽር መጀመሪያ ነው ።
እመ ቄሬኔዎስ መስፍን ለሶርያ ቄሬኔዎስ ለሶርያ ደጃዝማች ተሹሞ በነበረ ጊዜ እንድም ወውእቱ ጸሐፈ ቀዳሚ ይላል እብነት እሱ መጀመሪያ ቈጠረ።

፫ ወሖረ ኵሉ ሰብእ ይጸሐፍ በበ ሀገሩ ።

፫ ሰው ሁሉ በየሀገሩ ከግብር ይቈጠር ዘንድ ሔደ ።

፬ ወዓርገ ዮሴፍኒ እምገሊላ እምሀገረ ናዝሬት መንገለ ይሁዳ ኀበ ሀገረ ዳዊት እንተ ስማ ቤተ ልሔም ። ፩ ነገ ፳፮ ሚክ ፭ ፣ ፪ ፣ ማቴ ፣ ፪፥ ፮።

፬ ዮሴፍም ናዝሬት ከምትባል ሀገር ከገሊላ ቤተ ልሔም ወደምትባል የዳዊት ሀገር ወደ ምትሆን ወደ ይሁዳ ወጣ ።
እስመ ውእቱ ኮነ እምቤተ ዳዊት ውእቱ ።
ከዳዊት ወገን ነውና ።
ወእምአዝማደ ቤቱ ውእቱ ።
ከዘመዶቹ ወገን ነውና ።

፭ ወሖረ ይጸሐፍ ምስለ ማርያም እንተ ፈኃሩሎቱ እንዘ ፅንስት ይእቲ ።
ሖረ ምስለ ማርያም ይጸሐፍ ምስለ ማርያም ብለህ ግጠም ።

፭ ከጮኛው ከመቤታችን ጋራ ጸንሳ ሳለች ይቈጠር ዘንድ ሄደ ።

፮ ወእምዝ እንዘ ሀለዉ ህየ በጽሐ ዕለተ ወሊዶታ ።

፮ ከዚህ በኋላ በዚያ ሳሉ የምትወልድበት ጊዜ ደረሰ ።

፯ ወወለደት ወልደ ዘበኵራ ።

፯ የበኵር ልጅዋን ወለደች ።
ወአሠረቶ መንኮብያቲሁ ።
አውራ ጣቱን አሠረችው ሐተታ ፣ያጸናዋልና ፣ ምትሐት እንዳይደለ ለማጠየቅ እንድም በዛሬ ልማድ እንድም ዮሴፍ ኒቆዲሞስ እንዲህ አድርገው ይገንዙሃል ስትል ።
ወአስከበቶ ውስተ ጎል ።
በበረት አኖረችው እስመ አልቦሙ መካን ለማኀደሮሙ ብሎ እንዲያመጣው ቦታ የላቸውምና እንድም ላሕምኒ እእመረ ዘአጥረዮ አድግኒ ምቅማሆ ይላል ፣ እህያ ላህም አምኃ አስትንፋስን ገበሩ የሚል ነው ፣ አስተማወቅዎ እስትንፋስ አድግ ወላህም በመዋዕለ ቍር እንዲል ።
ወጠብለሎቶ በአጽርቅት ።
በጨርቅ ጠቀለለችው ብታጣ እንድም ምትሐት እንዳይደለ ለማጠየቅ ። እንድም ዮሴፍ ኒቆዲሞስ በድርብ በፍታ እንዲህ ይገንዙሃል ስትል እንድም ካህናት ዕለት ዕለት ሥጋህን ይጠቀልሉታል ስትል
እስመ አልቦሙ መካን ውስተ ማኀደሮሙ ።
ለማደሪያቸው ቦታ አልነበራቸውምና አስከበቶ ላለው

፰ ወሀለው ናሎት ውስተ ውእቱ ብሔር ይትጋሑ ወይሄልው

፰ በዚያ ሀገር ተግተው የሚጠብቁ ጠባቆች ነበሩ ።
ወየዓቅቡ መራዕዩሆሙ ሌሊተ በበዕብሬቶሙ ።
በየፈረቃቸው ተግተው መንጋቸውን የሚጠብቁ ፤ ሐተታ ቀዳማይ አካች ካልዓይ አካች ሣልሳይ አካች ። ራብዓይ አካች እንዲሉ ዐሥራ ሁለቱን ሰዓተ መዓልት ካራት ተካፍለው ይጠብቃሉ ሦስት ሦስት ይደርሳቸዋልና በበዕብሬቶሙ አለ ።

፱ ወናሁ ቆመ መልአከ እግዚአብሔር ኀቤሆሙ ።

፱ እነሆ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ባጠገባቸው ቆመ ።
ወስብሐተ እግዚአብሔር ሠረቀ ላዕሌሆሙ ።
ከቤተ ልሔም እሳቸው እስካሉበት ድረስ ባሕረ ብርሃን ፈሰሰላቸው እንድም በረቀ ይላል አልፎ አልፎ እንደ መስቀል መብራት ቦግ ቦግ ብሎ ታየ።
ወፈርሁ ዓቢየ ፍርሃተ ።
ፈጽመው ፈሩ ።

፲ ወይቤሎሙ መልአክ ኢትፍርሁ ።

፲ መልአኩ አይዟችሁ አትፍሩ አላቸው ።
እስመ ናሁ እዜንወክሙ ዐቢየ ዜና ዘይከውን ፍሥሐ ለክሙ ወላኵሉ ሕዝብ ።
ሐተታ ለመልአኩ ፍርሃት አርቆ መናገር ልማድ ነው ኢትፍራህ ዘካርያስ እንዲል ። እናንተን ስጡንም ሁሉ ደስ የሚያሰኝ ነገር እነግራችኋለሁ ።

፲፩ እስመ ናሁ ተወልደ ለክሙ ዮም መድኅን ዘውእቱ ክርስቶስ እግዚእ ቡሩክ በሀገረ ዳዊት ።

፲፩ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚያድል የዓለም መድኃኒት የሚሆን የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ በዳዊት ከተማ በዳዊት ባሕርይ ተወልዷልና ።

፲፪ ወከመዝ ትእምርቱ ለክሙ ።

፲፪ ምልክቱ ይህ ነው ።
ትረክቡ ሕፃነ እሡረ መንኮብያቲሁ ።
ሕፃኑ አውራ ጣቱን ታስሮ ወጥብሉለ በአጽርቅት በጨርቅ ተጠቅሎ ።

ወስኩብ ውስተ ጎል ፤
በበረት ተኛሎ ታገኙታላችሁ ።

፲፫ ወግብተ መጽኡ ምስለ ውእቱ መልአክ ብዙኃን ሐራ ሰማይ ።

፲፫ ከዚያ መልአክ ጋራ ብዙ መላእክት ነጉደው ሲመጡ ተሰሙ ።
ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ።

፲፬ ወይብሉ ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት
፲፬ አምላክ ለሆነ ሥጋ ከሥላሴ ጋራ ባንድነት ምስጋና ይገባዋል ወሰላም በምድር ለዕጓለ እመሕያው ሥምረቱ ።
የሰው ግዕዛኑ ይሰጠው ዘንድ በምድርም ዕርቅ ተወጠነ እያሉ ፩ም ስብሐት ለእግዚአብሔር እያልክ መልስ ንባብ አትሻ አምላክ ሰው ሆነ ።
ወሰላም በምድር
ሰው አምላክ ሆነ እያሉ ።
ሥምረቱ ለሰብእ ።
የሰው ፍቅር አገብሮት አምላክ ሰው ቢሆን ሰው አምላክ ሆነ ላሰው ። አንድም ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት በመላእክት ዘንድ ምስጋና ተደረገ በበታቸው በልዕልናቸው ሰማያት አላቸው ። ወሰላም በምድር ወደቂቀ አዳም ዘንድ አንድነት ሆነ ። የም አሐዱ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን እንዲል መላእክት ከኖሎት ኖሎት ከመላእክት ጋራ አንድ ሁነው አመስግነዋልና ለዕጓለ እመሕያው ሥምረቱ የሰው ፍቅር አገብሮት አምላክ ሰው ቢሆን የሁለቱም መፍቻ ።

፲፭ ወእምዝ ዓሪጎሙ መላእክት እምኅቤሆሙ ውስተ ሰማይ ።
፲፭ መላእክት ከሳቸው ተለይተው ወደሰማይ ከወጡ በኋላ ።
ይቤሉ እሙንቱ ሰብእ ኖሎት ንሑር እስከ ቤተ ልሔም ።
እነዚያ ጠባቆች እስከ ቤተ ልሔም ድረስ እንሂድ።
ወናእምር ዘንተ ነገረ ዘአርአየነ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር የገለጸልንን ነገር እንወቅ አሉ ። ሐተታ ከዚያ መልአክ አለ ከዚህ እግዚአብሔር አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም መልአክ ካለበት እግዚአብሔር እግዚአብሔር ካለበት መልአክ አይለይምና ።
፲፮ ወሖሩ ፍጡነ ።
፲፮ ፈጥነው ሄዱ ።
ወረከብዎሙ ለማርያም ወለዮሴፍ ።
ዮሴፍንና እመቤታችንን
ወሕፃንኒ ይሰክብ ውስተ ጎል ሕፃኑንም በጎል ተኝቶ አገኙዋቸው ።

፲፯ ወርእዮሙ አእመሩ ከመ በእንተ ሕፃን ዘነገርዎሙ ።

፲፯ አይተው የነገሯቸው ስለ ሕፃኑ እንደ ሆነ አወቁ ።

፲፰ ወኵሎሙ እለ ሰምዑ አንከሩ ዘነገርዎሙ ኖሎት ።

፲፰ መላእክት የነገሯቸው ኖሎት አይተው ። እንድም የነገሯቸው ኖሎት አይተው እንድም ኖሎት የነገሯቸው ሌሎች ሰምተው አደነቁ ።

፲፱ ወማርያምሰ ተዓቀበ ዘንተ ኵሎ ነገረ ወትወድዮ ውስተ ልባ ።

፲፱ እመቤታችን ግን ይህን ነገር ታስተውለው ነበር በልቡናዋም ታኖረው ነበር ።

፳ ወተመይጡ ኖሎት እንዘ ይሴብሕዎ ወየአኵትዎ ለእግዚአብሔር በእንተ ኵሉ ዘርእዩ ወሰምዑ ዘከመ ይቤልዎሙ ።

፳ እንደ ነገሯቸው ስላዩት ስለሰሙት ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑት ጠባቆች ተመለሱ ። እንዲህ ያለ ምሥጢር የገለጽክልን ተመስገን እያሉ ።

ዘከመ ተገዝረ ኢየሱስ ወዘከመ አቀምዎ
ውስተ ቤተ መቅደስ ።

፳፩ ወአመ ተፈጸመ ሰሙነ ዕለት ወሰድዎ ለሕፃን ከመ ይግዝርዎ ዘፍ. ፲፯፥፲፪ ዘሌዋ. ፲፪፥፫ ማቴ ፩፥፳፩ ሉቃ ፩፥፴፩ ።
በስምንተኛው ቀን ሊገዝሩት ወሰዱት ።
ወሰመይዎ ስሞ ኢየሱስ በከመ ሰመዮ መልአክ እምቅድመ ትፅንሶ በከርሣ ።
መልአኩ ሳትጸንሰው ኢየሱስ ትዪዋለሽ ብሎ እንደ ተናገረ ስሙንም ኢየሱስ ይሉት ዘንድ ። ሐተታ ዮሐንስን የሊቀ ካህናት ልጅ ነው ብለው አክብረው ሊገዝሩት መጡ አለ ፤ ጌታ ግን መምጣቱ ለትሕትና ነው እንጂ ለልዕልና አይደለምና ወሰዱት አለ ፤ ሃይማኖተ አበው ዝንቱ ዘተገዝረ አመ ሳምን ዕለት ዝንቱ ዘገዘርዎ በሥርዓተ ሕፃናት ይላል ስንክሣር አልተገዘረም አለ ። እንደምን ነው አይጣለም ቢሉ አይጣላም ። ስንክሣር ምን ቁም ነገር ነው ነገር እንደ ሃይማኖተ አበው ነው ፤ ይህስ ስንክሣርን መንቀፍ ሃይማኖተ አበውንም መንቀፍ ነው መላሻቸው አንድ ነው ብሎ ገዛሪው ምላጭ ይዞ ቀርቧል ወዳጄ ልትገዝረኝ መጣህ ቢለው ምላጩ እንደ ሰም ቀልጦበታል ከዕለተ ዓርብ እስቀድሞ ደሙ አይፈስምና እሱ በተአምራት ተገዝሯል ሃይማኖተ አበው መገዘሩን ሲያይ ተገዘረ አለ ። ስንክሣር በገዛሪ እጅ አለመገዘሩን ሲያይ አልተገዘረም አለ ።

፳፪ ወአመ ተፈጸመ ዕድሜ ንጽሖሙ ዘሌ ፲፪ ፭ ዘፀ ፲፫፥፪ ዘኁ ፰፥፲፭ ።

፳፪ ከሕርስ ደም የሚነጹበት ቀን በደረሰ ጊዜ ሐተታ ፣ በሌሎች ሴቶች ልማድ መናገር ነው እንጂ በመቤታችንስ ይህ ሁሉ የለባትም አንድም ከሰው የሚለዩበት ቀን በተፈጸመ ጊዜ ለወንድ ባርባ ቀን ለሴት በሰማንያ ቀን ።
በከመ ሕገ ሙሴ ወሰድዎ ኢየሩሳሌም ያቅምዎ ቅድመ እግዚአብሔር ።
ከእግዚአብሔር ፊት ሊያቆሙት ማለት እንደ ኦሪት ሥርዓት አጅ ያስነሱት ዘንድ ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት ።

፳፫ በከመ ጽሑፍ ውስተ ሕገ እግዚአብሔር ኵሉ ተባዕት ዘይፈትሕ ማኅፀነ እሙ ቅዱሰ ይሰመይ ለእግዚአብሔር ።

፳፫ በኵር ሁኖ የሚወለደው ሁሉ የእግዚአብሔር ልዩ አገልጋይ ይባላል ተብሎ በኦሪት እንደ ተጻፈ ። ሐተታ ፈታሒውስ አባቱ ነው መገለጫውን ሲያይ እንዲህ አለ እንጂ ።

፳፬ ወከመ ያብኡ መሥዋዕተ በከመ ተብሀለ ውስተ ሕገ እግዚአብሔር ።

፳፬ በኦሪት እንደ ተነገረ ስለ እሱ መሥዋዕት ያቀርቡለት ዘንድ ።
ዘውገ ማዕነቅ ።
የዋኖስ ወገን ቡላል ፣ የቡላል ወገን ዋኖስ አንድም ሁለት ቡላል ሁለት ዋኖስ ዘውገ እልባስ እንዲል ።
ወእመ አኮ ክልኤቲ ዕጕለ ርግብ ።
ይህም ባይገኝ ሁለት ርግብ ሊሠውለት ሐተታ ፤ አንዱን ሠውቶ ውሃ በብርት አድርጎ ደሟን ይቀበለዋል ባንዱቱ እየነከረ ይረጭባታልእስሚዝ እንዶድ አውባን ቅጠል የተጕነጐነ ሐር ጽሕመ ጠሊ ጨምሮ ይረጭበታል ኋላ ፈትቶ ከበረሐ ወስዶ ይጥላታል የተሰዋችዪቱ የጽድቅ የወንጌል ያልተሠዋችዪቱ የኦሪት የኃጢአት ምሳሌ ።

፳፭ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ በኢየሩሳሌም ዘስሙ ስምዖን ።

፳፭ በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል አንድ ሰው ነበረ ።
ወውእቱ ጻድቅ ።
እሱም ደግ ።
ወየዋሀ ።
ቅን ኃዳጊ በቀል ነበረ ።
ወይሴፈው ይርአይ ፍሥሐሆሙ ወመድኃኒቶሙ ለእሥራኤል ።
የእሥራኤልን ድኅነት ያይ ዘንድ ተስፋ ያደርግ ነበረ ።
ወመንፈስ ቅዱስ ላዕሌሁ ።
መንፈስ ቅዱስ አድሮበታል ያደረበት ነበር ።

፳፮ ወአርአዮ መንፈስ ቅዱስ ከመ ኢይመውት ዘእንበለ ይርአይ መሲሐ ለእግዚአብሔር ።

፳፮ እግዚአብሔር በተዋሕዶ ያከበረው ወልድን ሳያይ እንዳይሞት መንፈስ ቅዱስ ነግሮት ነበር ።

ታሪክ ፤ በጥሊሞስ የሚባል ገናና ንጉሥ ነበረ ከገናንነቱ የተነሣ ይህን ዓለም እንደ ሰም አቅልጦ እንደ ገል ቀጥቅጦ ገዝቶታል ያገሩን ሁሉ ቋንቋ ያውቅ ነበር ። ምን ቀረኝ ብሎ ጠየቀ ብዙ ጥበብ ብዙ ምሳሌ ያለባቸው አርባ ስድስቱ መጻሕፍተ ብሉያት ቀርተውሃል አሉት በዚያ ወራት በእሥራኤል ሠልጥኖባቸዋልና ጸሐፍቱንም መጻሕፍቱንም ስደዱልኝ ብሎ ላከ አርባ ስድስቱን መጻሕፍተ ብሉያት ሰባ ሁለት ጸሐፍት አድርገው ሰደዱለት ሁለቱ ከመንገድ ሙተው ቀርተዋል ለሰባው የሚላካቸው አንድ አንድ ብላቴና እያደረገ ለሁለት ለሁለት እንዳንድ ድንኳን ሰጣቸው ሠላሳ አምስት ይሆናል ታናናሹን እንዳንድ ደጋጉን ለሁለት ለሁለት የዕብራይስጡን በጽርዕ ቋንቋ ጻፉ ብሎ ሰጣቸው ።

መጽሐፈ ኢሳይያስ ለስምዖን ደረሰው ።ሲጽፍ ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ከሚለው አንቀጽ ደረሰ ። ድንግል በድንግልና ትጸንሳለች በድንግልና ትወልዳለች ብዬ ብጽፍ ስንኳን የአሕዛብ ንጉሥ የእሥራኤልስ ንጉሥ ቢሆን ይቀበለኛል ብሎ ወለት ትጸንስ ብሎ ጻፈ ። እንቅልፍ መጥቶበት ተኝቶ ቢነቃ ወለትን ፍቆ ድንግልን ጽፎ አገኘ ። ድንግልን ፍቆ ወለት ብሎ ጻፈ ። ሁለተኛ እንቅልፍ መጥቶበት ተኛ ቢነቃ ወለትን ፍቆ ድንግልን ጽፎ አገኘው ድንግልን ፍቶ ወለትን ጽፎ ሦስተኛ እንቅልፍ መጥቶበት ተኛ ቢነቃ ወለትን ፍቆ ድንግልን ጽፎ አገኘው ። እፍቃለሁ ቢል ኢትመውት ዘእንበለ ትርአይ መሲሐ ለእግዚአብሔር ብሎ ይህን ነግሮታል እንዲህ መሆኑ ስለምን ነው ቢሉ ውስጡ ጥበበ እግዚአብሔር ነው ። በዕብራይስጥ የተጻፉትን ዓላውያን የሚያቃጽሏቸው ናቸውና ።

በዕብራይስጥ የተጻፉት ሲጠፉ በጽርዕ የተጻፉት እንዲገኙ አድርጓል ። ዘመኑ አምስት መቶ ነው ያሉ እንደሆነ ይህን ሲጽፍ ሁለት መቶ አምሳ ሁለት ነበር ይህን ከጻፈ በኋላ ሁለት መቶ አምሳ ኖሯል ሦስት መቶ ነው ያሉ እንደሆነ ይህን ሲጽፍ መቶ አምሳ ሁኖት ነበር ይህን ከጻፈ በኋላ መቶ አምሳ ዘመን ኖሯል ። መምር ኤስድርስ ግን ይህን ሲጽፍ ያስራምስት ዓመት ብላቴና ነበር ብለዋል ።

፳፯ ወወሰዶ መንፈስ ምኵራብ ፤

፳፯ ካልኣ ተማብቆ ሲኖር መንፈስ ቅዱስ እንሣሥቶ አጸናንቶ ወደምኵራብ ወሰደው ወሶበ አብዕም አዝማዲሁ ለሕፃን እግዚእ ኢየሱስ ከመ ይግበሩ ሎቱ ዘበሕጉ ።

በአሪት እንደ ታዘዘ ያደርጉለት ዘንድ ብላቴናውን ዮሴፍና እመቤታችን ወደ ቤተ መቅደስ ባገቡት ጊዜ ።

፳፰ ተወከፎ ውእቱኒ ወአንበሮ ውስተ ሕፃኑ

፳፰ እሱ ተቀብሎ አቀፈው ።
ወባረኮ ለእግዚአብሔር ።
ከዚህ ጊዜ ያደረሰከኝ ከደዌዬ የፈወሰከኝ ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነው ።

፳፱ ወይቤ ይእዜ ትሥዕሮ ለገብርከ ።

፳፱ በታቀፈው ጊዜ ታድሷል ወደኸው እንደሆነ ከዚህ ላኑርህ አለው ባሪህን ዛሬ በሞት ታሰናብተዋለህ ትሥዕሮ ልታሰናብተው ይገባል ሠዓሮ አሰናብተው በሰላም ።
ፃር ጋር ሳይፀናብኝ በሽማግሌ ፃር ጋር ይፀናልና።

፴ እግዚእ በከመ አዘዝከ ።

፴ ሰሚዑ አብ ነው ያሉ እንደ ሆነ አቤቱ ኢትመውት ዘእንበለ ትርአይ መሲሐ ለእግዚአብሔር ብለህ እንደ ተናገርከ ።

፴፩ እስመ ርእያ አዕይንትየ አድኅኖተከ ። ዘአስተዳሎከ ቅድመ ኵሉ ሕዝብከ ።

፴፩ ለወገኖችህ ፊት ያዘጋጀኸውን አድኅኖትህ ወልድን አይቻለሁና ።

እንድም ሦስት አመት ከሦስት ወር ከሚያዩት አስቀድሞ ያዘጋጀኸው አድኅኖትህ ወልድን አይቻለሁና እንድም ሰሚው ወልድ ነው ያሉ እንደሆነ ።
በከመ አዘዝከ ።
መሬት አንተ ብለህ እንደተናገርከ ይህ የሁሉ ነው በወገኖችህ ፊት ያዘጋጀኸውን አድኅኖትህን አይቻለሁና እንድም ሦስትም ዓመት ከሦስት ወር ከሚያዩት ተአምራት አስቀድሞ ያዘጋጀኸውን አድኅኖትኸን አይቻለሁና ።

፴፪ ከመ ትክሥት ብርሃነ ለአሕዛብ ።

፴፪ ለኦሕዛብ ትንቢትን ተሰፋን ትገልጽ ዘንድ፤ ወክብረ ለሕዝብከ እሥራኤል ።
ለእሥራኤል ሃይማኖትን ልጅነትን ትገልጽ ዘንድ ።
ሐተታ እንዲህ ማለት ማካፈል አይደለም በወንጌል ካመኑ በኋላ ሁሉም በሁሉ ያሉ ናቸው የሌለ የሌላቸውን ሰጥቶ መናገር ነው እንጂ ።

፴፫ ወዮሴፍስ ወእሙ ያነክሩ በእንተ ዘነበበ ላዕሌሁ ።

፴፫ እመቤታችንና ዮሴፍ ግን ስለሚናገረው ነገር የሚናገረውን ነገር ያደንቃሉ ። ሐተታ ይህ አረጋዊ ፀንቶ እንዲህ ያለ ነገር ይናገራል ብለው ። እንድም ስለዚህ ሕፃን እንዲህ ይናገራል ብለው ስጌታ ስለሚናገረው አደነቁ ።

፴፬ ወባረኮሙ ስምዖን ።

፴፬ ስምዖን መረቃቸው ። ኢሳ ፡ ፰ ፡ ፲፬፣ ሮሜ ፱ ፴፪፥፩ ጴጥ፡፪ ፯ ወይቤላ ለእሙ ማርያም ናሁ ዝንቱ ሕፃን ሥዩም ለድቀቶሙ ወለተንሥኦቶሙ ለብዙኃን እምውስተ እሥራኤል እናቱን ማርያም ሆይ ይህ ሕፃን ከእሥራኤል ወገን ለብዙ ሰዎች ለልማታቸው ለጥፋታቸውም ንቡር ድልው ነው ።
ወለትእምርት በዘይትወቀሱ በሚፈረድባቸው ገንዘብ ይፈረድባቸው ዘንድ ።

፴፭ ወለኪሰ ይበውእ ውስተ ነፍስኪ ኲናተ ኑፋቄ ።

፴፭ ባንቺ ግን ባንቺም እንደ ጦር የሚከፍል ኃዘን በልብሽ ያድራልና አንድም ወለነፍስ አንተ ትበውእ ኲናት ይላል ጽብነት የጌታ ሞት እንደ ጦር የምትሰማ ኃዘን ናት ። አንድም ወለነፍስ አንተ ትበውእ ውስተ ኲናት ይላል እብነት ፀጥጦስ ጦር ለምትከበብ ለአይሁድ ስውነት ለልማታቸውም ለጥፋታቸውም ንቡር ድልው ነው ማለት የተዘጋጀ ነው ።
ከመ ይክሥት ሕሊና ልቦሙ ለብዙኃን ።
የብዙ ሰዎችን ሐሊና ይገልጽ ዘንድ ማለት የምእመናን ልቡና በደስታ ይገልጽ ዘንድ

፴፮ ወሀለወት ሐና ነቢይት ወለተ ፋኑኤል እንተ እምነገደ አሴር ።

፴፮ ከነገደ አሴር የተወለደች የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል ነቢይት ነበረች ።
ወኃለፈ መዋዕሊሃ ።
የሕፃንነቷ ዘመን አልፏል ።
ወምስለ ምታሰ ነበረት ሰብዓተ ክረምተ እምድኅረ ነበረት በድንግልናሃ ።
በድንግልና ዐሥራ አምስት ዓመት ከኖረች በኋላ ባል አግብታ ሰባት ዓመት ኖረች ።

፴፯ ወኮነት መበለተ ሰማንያ ወአርባዕተ ክረምተ ።

፴፯ ሰማንያ አራት ዓመት ፊት ሁና ኖረች ። ሐተታ መላው መቶ ስድስት ዓመት ይሆናል በጐ የበላች ባልቴት ናት ።
ወኢትወፅእ እምኵራብ መዓልተ ወሌሊተ እንዘ ትትቀነይ በጾም ወበጸሎት ።
በጾም በጸሎት ተወስና እግዚአብሔርን ስታገለግል በመዓልትም በሌሊትም ከምኵራብ አትወጣም ነበር ። ሕገ ሥጋ ጠፍቶላታል ቢሉ የተመቸ አል ከፋላትም ቢሉ እየወጣች እየገባች ።

፴፰ ወተንሥአት ሶቤሃ ወገነየት ።

፴፰ ፈጥና ተነሥታ አመነች ።
ወእእኰተቶ ለእግዚአብሔር ፤ እግዚአብሔርን አመሰገነችው ። ወነገረት በእንቲአሁ ለኵሎሙ እለ ይሴፈው መድኃኒታ ለኢየሩሳሌም ።

የኢየሩሳሌምን ድኅነት ተስፋ ለሚያደርጉ ሁሉ የብላቴናውን ነገር ተናገረች ።

በእንተ ኢየሱስ ሕፃን ።

፴፱ ወፈጺሞሙ ኵሎ ዘበሕገ ኦሪት አተው ገሊላ ሀገሮሙ ናዝሬተ ።

፴፱ በኦሪት የታዘዘውን በዓል እከብረው ከጨረሱ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ።

፵ ወልሀቀ ሕፃን ።
፵ ሕፃኑ አደገ ።
ወፀንዓ በመንፈስ ቅዱስ ። የሚያሳድግ ብቻ ማቢታ አይደለም ኃይል እልጎቂተ ኵሉ አለችና በመንፈስ ቅዱስ ጸና ።
ወምሉአ ጥበበ ጥበብን ተመልቶ ።
ወፍጹም በጸጋ እግዚአብሔር ዘላዕሌሁ ።
የእግዚአብሔር ጸጋ በርሱ ነበረች ማለት በርትዓተ መለያልይ አደገ አንድም ወምሉአ ጥበበ ጥበብ መንፈሳዊን ተመልቶ ወበጸጋ ልሕቃንሰ በአካል ዘሥጋ ነፍሱን ትበርህ በጥበብ ወበጸጋ ዝኒ ከመ አዳም ቀዳማዊ ባለው አደገ ።

ዘከመ ረፈቀ ኢየሱስ ማእከለ ሊቃውንት ።

፵፩ ወየሐውሩ አዝማዲሁ ኢየሩሳሌም ለለዓመት ለበዓለ ፋሲካ ። ዘፀ ፳፫ ፣ ፲፭፤ዘዳ ፲፮ ፩ ።

፵፩ እመቤታችንና ዮሴፍ ባመት ባመት በዓል ለማክበር ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር ።

፵፪ ወአመ ኮኖ ፍጹመ ሎቱ ፲ቱ ወ፪ቱ ክረምቱ
፵፪ ዐሥራሁለት ዓመት ሲመላው ዓርጉ ለበዓል ኢየሩሳሌም በከመ ያለምዱ ።
እንዳለመዱ በዓለ ፋሲካውን ለማክበር ኢየሩሳሌም ወጡ ።

፵፫ ወሠሊጦሙ ግብሮሙ አተው ገሊላ ሀገሮሙ
፵፫ በዓሉን ካከበሩ በኋላ ወደሀገራቸው ተመለሱ
ወሕፃንሰ ኢየሱስ ነበረ ኢየሩሳሌም ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በኢየሩሳሌም ቀረ። ነበረ ውስተ ገሊላ እንዲል ተርፈ ሲል ወኢያእመሩ ዮሴፍ ወእሙ እመቤታችንና ዮሴፍ ግን እንደቀረ ዐላወቁም ።

፵፬ ወይመስሎሙ ከመ ዘበፍኖት ሀሎ ምስለ ሰብእ ።

፵፬ በፊት ከሄዱ ሰዎች ጋራ ያለ መሰላቸው ነበር ። ሐተታ ያገኘው ሁሉ ይነጣጠቀው ነበርና፤ ወበጺሖሙ ኃሠሥዎ በዕለታ ኀበ አዝማዲሁ ወኀበ እለ የእምርዎ ። በደረሱም ጊዜ ከዘመዶቹና ከሚያውቁት ዘንድ ዕለቱን ፈለጉት ።
ወኢረከብዎ ። እላገኙትም ።

፵፭ ወሶበ ኢረከብዎ ኅሠሠሡ ኢየሩሳሌም እንዘ የኃሥሥዎ ።

፵፭ ባያገኙት እየፈለጉ ወደኢየሩሳሌም ተመለሱ ።

ወእምዝ በሣልስታ ረከብዎ

፵፮ እንዘ ይነብር በማእከለ ሊቃናት
፵፮ ከዚህ በኋላ በሦስተኛው ቀን በሊቃነ ካህናት መካከል ተቀምጦ አገኙት ።
ወያጸምዖሙ ።
ሲሰማቸው ።
ወይሴእሎሙ ።
ሲጠይቃቸው እንድም ያጸምዖሙ አጥብቆ ሲያሰማቸው ሲጠይቃቸው ፤

፵፯ ወያነክርዎ ኵሎሙ እለ ሰምዑ ጥበቦ ወአውሥኦቶ ።

፵፯ ጥያቄውን ምላሹን የሰሙ ሁሉ ያደንቁት ነበር ።

፵፰ ወሶበ ርእይዎ ደንገፁ ፤

፵፰ ባዩት ጊዜም ደነገጡ ልጅ ከሽማግሌ መካከል ተቀምጦ ሲያፈችል ቢገኝ ያስደነግጣልና ወትቤሎ እሙ ወልድየ ለምንት ከመዝ ረሰይከነ፤ እናቱ እመቤታችን ልጄ ለምን እንዲህ አደረግኸን፥ እስመ ናሁ አቡከኒ ወአነኒ ሠራሕነ እንዘ ነሐሥሥከ። እኔና ዮሴፍ ስንፈልግህ ደከምን አለችው ።

፵፱ ወይቤሎሙ ለምንት ተሐሥሡኒ ።
፵፱ ለምን ትፈልጉኛላችሁ ።
ኢያእመርክሙኑ ከመ ይደልወኒ እሀሉ ውስተ ዘአቡየ ቤት ባባቴ ቤት በዚህ ዓለም በምልአት መኖር እንዲገባኝ እላወቃችሁምን ። አንድም በቤተ መቅደስ መኖር እንዲገባኝ አታውቁምን አላቸው ።

፶ ወእሙንቱስ ኢለበው ቃሎ ዘይቤሎሙ ።
፶ እሳቸው ግን በምልአት ያላቸውን ነገር እላስተዋሉትም ነበር ዮሴፍን ሲያይ ነው እንጂ እመቤታችንስ ታውቃለች ።

፶፩ ወሖረ ወወረደ ምስሌሆሙ ናዝሬተ ።
፶፩ ከሳቸው ጋራ ወደናዝሬት ሄደ ።
ወኮነ ይትኤዘዝ ሎሙ ።
ያገለግላቸው ነበር ።
ወእሙስ ተዓቅብ ዘንተ ኵሎ ነገረ ።
እመቤታችን ግን ይህን ሁሉ ነገር ታስተውለው ነበር ወትወድዮ ውስተ ልባ ።
በልቡናዋ ታኖረው ነበር ።

፶፪ ወእግዚእ ኢየሱስ ልሀቀ ።
፶፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አደገ ።
ወዐብየ በጥበብ ወምክር ።
በጥበብ ጠባይዓዊ በምክር ጠባይዓዊ ። አንድም በጥበብ መንፈሳዊ በምክር መንፈሳዊ ።
ወበጸጋ ። በርትዓተ መለያልይ ልሀቃንሰ በአካል ዘሥጋ ነፍሱኒ ትበርህ በጥበብ ወበጸጋ ባለውም አደገ ።

በኀበ እግዚአብሔር ወበኀበ ሰብእ ። በእግዚአብሔርም ዘንድ በሰውም ዘንድ ማለት ፍቅረ ቢጽንና ፍቅረ እግዚአብሔርን ይዞ አደገ ።

በእንተ ስብከት ዘዮሐንስ መጥምቅ

ምዕራፍ ፫ ።

፩ ወአመ ፲ቱ ወኃምስቱ ዓመተ መንግሥቱ ለጢባርዮስ ቄሣር ፤

፩ ጢባርዮስ ቄሣር በነገሠ ባ፲፭ ዓመት ። ሐተታ ከአውግሥጦስ ቄሣር ፲፭ ዓመት ያመጣል ከጢባርዮስ ቄሣር ፲፭ በ፴ ዘመን ተጠመቀ ለማለት እንዲህ አለ ፣ የቍጥር መጽሐፍ አውግስጦስ ቄሣር በነገሠ ባ፵፪ ዓመት ተወለደ ይላል ። ቅዱስ ቄርሎስ አውግስጦስ በነገሠ በ፲፰ ዓመት ተወለደ ይላል ወንጌል ፲፭ ዓመት ያመጣል አለ ። አይጣላም ቢሉ አይጣላም ። የአውግስጦስ ቄሣር መላ ዘመን መንግሥቱ ፶፯ ነው ። በነገሠ በ፵፪ ዘመን ጌታ ተወልዷል ፲፭ና ፵፩ ፶፯ ይሆናል ። ቄርሎስ ፲፰ አለ በነገሠ በ፳፬ ዘመን ንጉሠ ነገሥትነት ደርሷል ንጉሠ ነገሥትነት ከደረሰ ጀምሮ ቈጥሮ ፲፰ አለ ። ፳፬ና ፲፰ ፵፪ ይሆናል አይጣላም ።
እንዘ ጲላጦስ ጴንጤናዊ መልአከ ይሁዳ ።

የጴንጤን ሰው ጲላጦስ በይሁዳ ተሹሞ ሳለ በተሾመ ጊዜ ወሄሮድስ ንጉሥ ሳዕለ ገሊላ ።
ሄሮድስ በገሊላ ነግሦ ሳለ በነገሠ ጊዜ ።
ወፊልጶስ እኁሁ መልአከ ኤጡርያስ ።
ወንድሙ ፊልጶስ በኤጡርያስ ነግሦ ሳለ በነገሠ ጊዜ።
ወስብሔረ ጥራኮኒዶስ ።
በጥራኮኒዶስም ተሹሞ ሳስ በተሾመ ጊዜ ።
ወሊላንዩ እንተ ሰብላኒስ ። ሊላንዩ በሰብላኒስ ተሹሞ ሳለ በተሾመ ጊዜ ፣ ሊሳንዩ ሀቢ እንተ ሳብላኔስ ይላል ሊሳንዩ ሀቢ በሰብላኒስ ተሾሞ ሳለ በተሾመ ጊዜ ፤ ፊልጶስ ባራቱ አህጉር ተሹሟል ። አንድም መልስ ላዕለ ራብዕት እዴሃ ለይሁዳ ይላል አብነት ጲላጦስ በይሁዳ በርቦዋ ተሹሞ ሳስ በተሾመ ጊዜ ፣ ሄሮድስ በገሊላ በርቦዋ ተሹሞ ሳለ በተሾመ ጊዜ ወፊልጶስ እኁሁ ላዕለ ራብዕተ እዴሃ ለኤጡርያስ ።

ወንድሙ ፊልጶስ በኢጡርያስ በርቦዋ ተሹሞ ሳለ በተሾመ ጊዜ ወሊሳንዩ ሀቢ ላዕለ ራብዕተ እዴሃ ለሰብላኒስ ።
ሊሳንዩስ ሀቢ በስብላኒስ በርቦዋ ተሹሞ ሳለ በተሾመ ጊዜ አንዱን አገር ካራት እየተካፈሉ ተሹመውታል ። ሳዕለ መንፈቀ መንፈቃ ይላል አብነት ትርጓሜው አይለወጥም ።

፪ ወአመ ሐና ወቀያፋ ሊቃነ ካህናት ።

፪ ሐና ቀያፋ ሊቃነ ካህናትነት ተሹመው ሳሉ በተሾሙ ጊዜ ሐተታ ። ሊቀ ካህናቱ አንድ አይደለም ቢሉ ምሉና ዱግ ሁነው ተሹመውታል ።
መጽአ ቃለ እግዚአብሔር ላዕለ ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ በገዳም ።
ከዘካርያስ ልጅ ከዮሐንስ ዘንድ በገዳም ሳለ ውጣ አስተምር የሚል ቃል ተሰማ ።

፫ ወዖደ አድያመ ዮርዳኖስ ወሰበከ ጥምቀተ ለንስሐ በዘይት ኀደግ ኃጢአት ። ማቴ ፡ ፫ ፩ ማር፡፩፡፬

፫ ኃጢአት በሚሰረይ ገንዘብ ይሰረይ ዘንድ በዮርዳኖስ ዙሪያ እየዞረ ለንስሐ ጥምቀትን አስተማረ

፬ በከመ ይብል ቃለ መጽሐፈ ኢሳይያስ ነቢይ ኢሳ፡ ፵ ፫ ዮሐ፡ ፩፡ ፳፫ ።

፬ የነቢዩ የኢሳይያስ መጽሐፍ እንደ ተናገረ ዘይቤ ናሁ ቃለ ዓዋዲ ዘይሰብክ በገዳም ዘይብል ጺሑ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርን መንገድ አዘጋጁ ።
ወአርዩ መጽያሕቶ ።
ጥርጊያውንም አስተካክሉ የሚል ያዋጅ ነጋሪ ቃል እነሆ በገዳም አለ የሚል ።

፭ ኵሉ ማዕምቅ ይምላእ ።
፭ ጎድጓዳው ሁሉ ይምላ ።
ወኵሉ ደብር ወወግር ይትሐት ተራራው ኰረብታው ሁሉ ይናድ ዝቅ ይበል ።
ወይኩን መብእስ መጽያሕተ ርቱዓ ።
ስንካላው መንገድ ጽርጊያ ይሁን ።
ወይእሪ ፍኖት መብእስ ።
ስንካላው ይተካከል ።
ወይርአይ ኵሉ ዘነፍስ አድኅኖቶ ለእግዚአብሔር። ሥጋዊ ደማዊ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ ይወቅ ሐተታ ንጉሥ በወጣበት ጊዜ ጕድጓዳው መልቶ ሥሩ ተነቅሎ ደንጊያው ተለቅሞ ለፈረስ ለሠረገላ እንዲመች ተደልድሎ ይቆያልና በዚያ ግሥ እንዲህ አለ ። ይህም አልቀረም ዘሩባቤል ከፋርስ ከባቢሎን በወጣ ጊዜ ይህ ሁሉ ተደርጓል ። አንድም ኵሉ ማዕምቅ እያልክ መልስ ። ተስፋ ያልያዘ ልቡና ተስፋ ይያዝ ።
ወኵሉ ወግር ። ጣዖታዊ ልቡና ጣዖቱን ይተው ።
ወይኩን መብእስ በጣዖት በኃጢአት የተሰናከለ ሰው ሁሉ ንጹሕ ይሁን ወይዕሪ ፍኖት መብእስ ሰው ሁሉ አንድ ወገን ሁኖ በሕገ ኦሪት ለእግዚአብሔር ይገዛ ።

፮ ወይርአይ ኵሉ ዘነፍስ ።

፮ ሰው ሁሉ ሚጠተ ሥጋውን ይይ ፣ አንድም ኵሉ ማዕምቅ ትሩፋን ከባቢሎን ይውጡ ።
ወኵሉ ወግር ። ባቢሎናውያን ይዋረዱ ከዚህ በላይ አይለወጥም ። አንድም ኵሉ ማዕምቅ ሐዋርያት ልዕልና ነፍስ ያግኙ ። ወኵሉ ወግር ። ጸሐፍት ፈሪሳውያን ይዋረዱ ። ወይኩን መብእስ በኃጢአት

የተሰናከለ ሰው ሁሉ ንጹሕ ይሁን ። ወይዕሪ ፍኖት መብእስ ። ሰው ሁሉ አንድ ወገን ሁኖ በሕገ ወንጌል ለእግዚአብሔር ይገዛ ወይርአይ ኵሉ ዘነፍስ ። ሥጋዊ ደማዊ ሰው ሁሉ ሚጠተ ነፍሱን ይወቅ ፤ አንድም ኵሉ ማዕምቅ ነፍሳት ይውጡ ወኵሉ ደብር ። ኢጋንንት ይዋረዱ ከዚህ በታች አይለወጥም አንድም ኵሉ ማዕምቅ ። ተስፋ ያልያዘ ልቡና ተስፋ ይያዝ ፣ ወኵሉ ደብር ። በምክረ ርእሱ በፈቃደ ርእሱ የሚኖር ሰው ሁሉ በምክረ ካህን ይኑር ወይኩን መብእሰ ፤ በኃጢአት የተሰናከለ ሰውነት ንጹሕ ይሁን ። ወይዕሪ ፍኖት መብእሰ ፣ ሰው ሁሉ አንድ ወገን ሁኖ በሕገ ወንጌል ለእግዚአብሔር ይገዛ ። ወይርአይ ኵሉ ዘነፍስ ። ሥጋዊ ደማዊ ሰው ሁሉ አድኅኖተ እግዚአብሔር ወልድ በእምሳለ ኅብስት እንዲሰጥ እንዲሠዋ ይወቅ ሲሰጥ ሲሠዋ ያስተውል ።

፯ ወይቤሎሙ ዮሐንስ ለሕዝብ እለ መጽኡ ኀቤሁ ያጥምቆሙ ኦ ትውልደ ሰበድዓት መኑ ነገረክሙ ታምሥጡ እመቅሠፍት ዘይመጽእ።ማቴ ፫፥፯

፯ ዮሐንስም ሊያጠምቃቸው የመጡትን ሕዝቡን እናንት የጉበና ልጆች ከሚመጣው መቅሠፍት ትድኑ ዘንድ ማን ነገራችሁ አላቸው ። ሐተታ ማቴዎስ ትውልደ አራዊተ ምድር ይላል ። ሉቃስ ትወልደ ሰበድዓት አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም የሁለት ቀን ትምህርት የልሳን መለያየት ነው ። አንድም ማቴዎስ የወል ስማቸውን ሉቃስ የጉልማ ስማቸውን ተናገረ ። አንድም የሰበድዓት ኅብሩ ብዙ እንደሆነ ቤተ አይሁድም ብዙ ኃጢአት ይሠራሉና ።

፰ ግበሩ እንከ ፍሬ ዘይደልወክሙ ለንስሐ ።
፰ ለማመን የሚያበቃችሁን ሥራ ሥሩ ።
ወኢይምሰልክሙ በብሂለ ዘትብሉ ሀሎ አቡነ አብርሃም ። አብርሃም አባታችን ነው በማለት አይምሰላችሁ ።
እብለክሙ ከመ ይክል እግዚአብሔር አንሥኦ ውሉደ ለአብርሃም እምእላንቱ እዕባን ።
እግዚአብሔር ከነዚህ ደንጋዮች ለአብርሃም ልጅ መተካት ይቻለዋል ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፱ እስመ ወድአ ተሠይመ ጕድብ ኀበ ጕንደ ዕፀው ።
፱ ገጀሞ በዛፎች ሥር ላይ ፈጽሞ ተቃጥቷልና ። ሐተታ ማቴዎስ ማኅጼ ይላል ከዚህ ጕድብ አለ እንደ ምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም የሁለት ቀን ትምህርት የልሳን መለያየት ነው ። አንድም ሥራው የገጀሞ ነውና ሉቃስ ጕድብ አለ ኦልቆር ጥለት ሲል አዞሮ ከላይ እንደ ምሳር አድርጐ ይሠራዋልና ያን ሲያይ ማቴዎስ ማኅጼ አለ ።
ወኵሉ ዕፅ ዘኢይፈሪ ፍሬ ሠናየ ይገዝምዎ ወውስተ እሳት ይወድይዎ ።
መልካም ፍሬ የማያፈራውን ዕንጨት ሁሉ ቆርጠው ከእሳት ይጥሉታል ።

፲ ወተስእልዎ ሕዝብ ወይቤልዎ ምንተ ንግበር
፲ ሕዝቡ ምን እናድርግ ብለው ጠየቁት ።
፲፩ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ዘቦ ክልኤ ልብስ ክዳናት የሀብ ለዘአልቦ ።

፲፩ ሁለት ልብስ ያለው መጐናጸፊያን ለሌለው ይስጥ ።
ወዘሂ እክል ቦ ከማሁ ለይግበር ።
እህል ያለውም ለሌለው ይስጥ ብሎ መለሰላቸው ።

፲፪ ወመጽኡ መጸብሐንሂ ያጥምቆሙ ።
፲፪ ቀራጮችም ሊያጠምቃቸው መጡ ።
ወተስእልዎ ወይቤልዎ ሊቅ ምንተ ንግበር ።
መሀምር ምን እናድርግ ብለው ጠየቁት ።

፲፫ ወይቤሎሙ አልቦ ግድፋዴ ዘትገብሩ እምዘተአዘዝክሙ ።

፲፫ ከታዘዛችሁት አትርፋችሁ አትሥሩ አላቸው
፲፬ ወተስእልዎ ሐራሂ ወይቤልዎ ንሕነኬ ምንተ ንግበር ።

፲፬ ጭፍሮችም እኛስ ምን እናድርግ ብለው ጠየቁት ።
ወይቤሎሙ ኢትትዓገሉ ወኢመነሂ ።
ማንንም ማንን አትበድሉ ።
ወኢትሂዱ ።   አትቀሙ
ወንበሩ በበሲሳይክሙ ።
ደመወዛችሁ ይብቃችሁ አላቸው ።
፲፭ ወሐለዩ ኵሉ ሕዝብ በልቦሙ ወመሰሎሙ ዮሐንስ ከመ ውእቱ ክርስቶስ ።
፲፭ ሕዝቡም ዮሐንስ ክርስቶስ እንደሆነ በልቡናቸው አሰቡ ።
፲፮ ወአውሥአ ዮሐንስ ወይቤሎሙ ለኵሎሙ አንሰ አጠምቀክሙ በማይ ።
፲፮ ዮሐንስም እኔስ በውሃ አጠምቃችኋለሁ ወይመጽእ ዘይጸንዓኒ ዘኢይደልወኒ እፍታሕ ቶታነ አሣዕኒሁ ። ማቴ ፫ ፲፩ ማር ፩ ፯ ዮሐ ፩ ፳፯ ግብ ፩ ፭ የጫማውን ማዘቢያ እፈታ ዘንድ የማይገባኝ ከኔ የሚበረታ ግን ይመጣል ብሎ መለሰላቸው ሐተታ፣ እጹር ማቴዎስ እድንን ማርቆስ እፍታሕ ሉቃስ መገናኛው ዮሐንስ ። እንዲህ ግን ስለሆነ አንድን ይቀድማል እፍታሕ ይከተላል እጹር መጨረሻ ነው ይህን ተካፍለው ጽፈዋል ።
ወውእቱ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወበእሳት።
እሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃችኋል ።
፲፯ ዘመስሔ ውስተ እዴሁ ወያነጽሕ ዐውደ እክሉ ።
፲፯ የእህሉን አውድማ የሚያጸራበት መንሽ በጁ ነው ።

ወያስተጋብእ ሥርናዮ ውስተ መዛግብቲሁ ።
ምንጄውን በጎተራ ይሰበስባል ወኃሠርሰ ያውዒ በእሳት ዘኢይጠፍዕ ።
ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል ።

፲፰ ወቦ ባዕድኒ ብዙኀ ዘመሀሮሙ ለሕዝብ
፲፰ ለሕዝቡ ያስተማራቸው ሌላም ብዙ አለ ።
ወባዕደኒ ብዙኃ መሐሮሙ ይላል ። ሌላ ትምህርት ንም አስተማራቸው አለ ጻግም ሕግን ።
ወገሠጾሙ ።
ይመክራቸው ነበር ።

ዘከመ ተሞቅሐ ዮሐንስ መጥምቅ ።

፲፱ ወኮነ ዮሐንስ ይጌሥጾ ለሄሮድስ ።
፲፱ ዮሐንስ ሄሮድስን ይገሥጸው ነበር ።
ወይዘልፎ በእንተ ሄሮድያዳ ብእሲተ ፊልጶስ እኁሁ።
ማቴ ፲፬ ፬ ማር ፮ ፲፯ ።
በወንድሙ በፊልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት ይዘልፈው ነበር ።
ወበእንተ ኵሉ እኩይ ዘገብረ ሄሮድስ ።
ሄሮድስ ስለሚሠራው ክፉ ነገር ሁሉ ይገሥጸው ነበር ። ሐተታ ሰውሮ ነፍስ ሳያስገድል አይውልም ነበር ። አንድም ግብረ ሰዶም ይሠራ ነበር ።
፳ ወዓዲ ወሰከ ።
፳ ሄሮድስ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ጨመረ
እንበይነ ዝኒ ተቀየሞ ለዮሐንስ ወዓፀዎ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ።
ስለዚህ ነገር ዮሐንስን ሳይዘልፈኝ አይቀርም ብሎ ተቀይሞ አጋዘው ። እንበይነ ዝኒቂም ስለዚህ ቂም አጋዘው አንድም ዮሐንስ በዘለፋ ላይ ዘለፋ ጨመረ ስለዚህ ተቀየመው አጋዘው ተቀይሞ አጋዘው ስለ ዚህ ቂም አጋዘው ።

በእንተ ጥምቀት ዘኢየሱስ ።

፳፩ ወእምድኅረ ተጠምቁ ኵሉ ሕዝብ ተጠ ምቀ እግዚእ ኢየሱስኒ ። ማቴ ፫ ፲፫ ። ማር ፩ ፲፱ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፴፪ ።
፳፩ ሕዝብ ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ተጠመቀ ። ሐተታ ጌታ ፊት ተጠምቆ ሕዝቡ በኋላ ተጠምቀው ቢሆን አሪት አላለፈችም ባንድነትም ተጠምቆ በሆነ ተቀላቅላ ትሠራለች ባሉ ነበርና ።
፳፪ ወእንዘ ይጼሊ ተርኅወ ሰማይ ማቴ ፡ ፫ ፲፯ ። ሉቃ ፱ ፴፭ ። ፪ ጴጥ ፩ ፡ ፲፯ ።
፳፪ ሲጸልይ ሰማይ ተከፈተ ። ወወረደ መን ፈስ ቅዱስ በአምሳለ ሥጋ ርእየተ ርግብ ጸዓዳ ። መንፈስ ቅዱስ መልክአ ርግብ ባለው ባሕርይ አምሳል ወረደ ወመጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል አንተ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ።
የምወድህ ልጄ አንተ ነህ የሚል ድምፅ መጣ ።
ወኪያከ ሠመርኩ ።
ደስታዬን ላይብህ የመረጥኩህ ።

በእንተ መጽሐፈ ትውልድ ዘኢየሱስ ።

፳፫ ወየአክል ሠላሳ ክረምቱ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፳፫ ጌታ በተጠመቀ ጊዜ ሠላሳ ዘመን ሆኖ ነበር ።

ወይመስሎሙ ወልደ ዮሴፍ ውእቱ ።
ምንም አንተ ውእቱ ወልድየ ብሎ ቢመሰክርለት ለሳቸው ። የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸው ነበር የዮሴፍ ልጅ ነው ይሉ ነበር ።

፳፬ ወልደ ኤሊ   የኤሊ ልጅ ።
፳፬ ወልደ ማቲ ።
የማቲ ልጅ ። ማቴዎስ ዮሴፍን ወልደ ማትያን ወልደ ያዕቆብ ይለዋል ። ከዚህ ሉቃስ ወልደ ኤሊ ወልደ ማቲ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ። ለዳዊት ናታን ሰሎሞን የሚባሉ ልጆች ነበሩት ማቴዎስ በሰሎሞን የወረደውን ቈጠረ ። ሉቃስ በናታን የወረደውን ቈጠረ ። ያውስ ቢሆን ላንድ ሰው ሁለት አባት አለውን ብሎ ማቴዎስ በልደት ሥጋዊ ቈጥሮ ሉቃስ በልደት ሕጋዊ ቈጥሮ ማቲ ሹሻን አግብቶ ኤሊን ወልዶ ይሞታል ። ማትያን እሷን አግብቶ ያዕቆብን ይወልዳል ኤሊና ያዕቆብ ወንድማማች ናቸው ኤሊ ታላቅ ነው ታላቅ ባለ ታናሽ እያገባምና ለኤሊ ሚስት አጋቡት እሱ ልጅ ሳይወልድ ሞተ ። አቅም ዘርዓ ለእኁከ ብለው ለያዕቆብ አጋቡት እሷን አግብቶ ዮሴፍን ይወልዳልና። አንድም የጌታ ልደቱ እንደ ማቴዎስ በልደት ሥጋዊ ። እንደ ሉቃስ በልደት ሕጋዊ አይደለምና ተሰያይተው ቈጠሩ ።
ወልደ ኤሊ ።   የኤሊ ልጅ
ወልደ ሜልኪ ።
የሜልኪ ልጅ ።
ወልደ ዮና ።   የዮና ልጅ
ወልደ ዮሴፍ ።   የዮሴፍ ልጅ

፳፭ ወልደ ማታትዩ ።
፳፭ የማታትዩ ልጅ ።
ወልደ አሞጽ ። የአሞጽ ልጅ
ወልደ ናሆም ። የናሆም ልጅ
ወልደ ኤስሎም ።
የኤስሎም ልጅ ።
ወልደ ናጌ ።   የናጌ ልጅ
፳፮ ወልደ ማአት ። የማአት ልጅ
ወልደ ማታትዩ ።
የማታትዩ ልጅ ።
ወልደ ሴሜይ ።   የሴሜይ ልጅ
ወልደ ዮሴፍ ።   የዮሴፍ ልጅ
ወልደ ዮዳ ።   የዮዳ ልጅ

፳፯ ወልደ ዮናን ። የዮና ልጅ ።
ወልደ ሬስ ። የሬስ ልጅ
ወልደ ዘሩባቤል ፤
የዘሩባቤል ልጅ ደግ ሰውነውና ደግነቱን ሲያይ ዘሩባቤልን አነሳው መንግሥት ከተለያየ በኋላ አሥራሁለቱን ነገድ አንድ አድርጎ ነግሦአልና ወያዕቆብስ ያስተኤሪ ንግሠ እንዲል ።
ወልደ ሰላትያል ።
የሰላትያል ልጅ ።
ወልደ ኔሪ ፤ የኔሪ ልጅ

፳፰ ወልደ ሜልኪ ፤

፳፰ የሜልኪ ልጅ ማቴዎስ ሰላትያልን ወለደ ኢኮንያን ወልደ ኤልያቄም ይለዋል ። ሉቃስ ወልደ ኔሪ ወልደ ሜልኪ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ። ለዳዊት ናታን ሰሎሞን የሚባሉ ልጆች ነበሩት ማቴዎስ በሰሎሞን የወረደውን ሉቃስ በናታን የወረደውን ቈጥሮ ነው ። ያውስ ቢሆን ላንድ ሰው ሁለት አባት አለውን ብሎ ማቴዎስ በልደት ሥጋዊ ሉቃስ በልደት ሕጋዊ ቈጥሮ እንዲህ አለ ። እንደም ሜልኪ ነጋሪን ሽታ ወለተ ኤልትማልም ዘኢየሩሳሌምን አግብቶ ኔሪን ወልዶ ይሞታል ። ኤልያቄም እሷን አግብቶ ኢኮንያንን ይወልዳል ። ሜሪና ኢኮንያን ወንድማማች ናቸው ኔሪ ታላቅ ነው ። ታላቅ ሳለ ታናሽ አያገባምና ለኔሪ ሚስት አጋቡት ልጅ ሳይወልድ ሞተ አቅም ዘርዓ ለአኁከ ብለው አጋቡት ኢኮንያን እሷን አግብቶ ሰላትያልን ይወልዳል ። አንድም የጌታ ልያቱ እንደ ማቴዎስ በልደት ሥጋዊ እንደ ሉቃስ በልደት ሕጋዊ አይደለምና ተለያይተው ቈጠሩ ።
ወልደ ሐዲ ፥ የሐዲ ልጅ
ወልደ ዮሳ ። የዮሳ ልጅ
ወልደ ቆሳም ፥ የቆሳም ልጅ
ወልደ ኤልሞዳም ።
የኤልሞዳም ልጅ ።
ወልደ ኤር ፥ የኤር ልጅ

፳፱ ወልደ ዮሴዕ ፥ የዮሴዕ ልጅ
ወልደ አልዓዛር የአልዓዛር ልጅ
ወልደ ማጣት የማጣት ልጅ
ወልደ ሌዊ ። የሌዊ ልጅ
፴ ወልደ ስምዖን ፤
፴ የስምዖን ልጅ ።
ወልደ ይሁዳ ። የይሁዳ ልጅ ፤
ወልደ ዮሴፍ ። የዮሴፍ ልጅ
ወልደ ዮናን ፥ የዮናን ልጅ ፤

ወልደ ኤልያቄም ።
የኤልያቄም ልጅ ።

፴፩ ወልደ ሜልያ ፥ የሜልያ ልጅ
ወልደ ማይናን ።
የማይናን ልጅ ፤
ወልደ ማጣት ፥ የማጣት ልጅ
ወልደ ናታን ። የናታን ልጅ
ወልደ ዳዊት ።
የዳዊት ልጅ ። ዳዊት መገናኛ

፴፪ ወልደ ዕሤይ ፥ የዕሤይ ልጅ
ወልደ ኢዮቤድ ።
የኢዮቤድ ልጅ ።
ወልደ ቡኤዝ ፤ የቡኤዝ ልጅ
ወልደ ሰልሞን ። የሰልሞን ልጅ
ወልደ ነአሶን ፥ የነአሶን ልጅ

፴፫ ወልደ አሚናዳብ ።
፴፫ የአሚናዳብ ልጅ ፥
ወልደ አራም ፥ የአራም ልጅ
ወልደ አርኒ ።
የአርኒ ልጅ ። አርኒ ትርፍ ነው
ወልደ ኤስሮም ።
የኤስሮም ልጅ ።
ወልደ ፋሬስ ። የፋሬስ ልጅ
ወልደ ይሁዳ ። የይሁዳ ልጅ

፴፬ ወልደ ያዕቆብ ፥ የያዕቆብ ልጅ
ወልደ ይስሐቅ ።
የይስሐቅ ልጅ።
ወልደ አብርሃም ።
የአብርሃም ልጅ ።
ወልደ ናኮር ፥ የናኮር ልጅ

፴፭ ወልደ ሴሩህ ። የሴሩህ ልጅ
፴፭ ወልደ ራግው ፥ የራግው ልጅ
ወልደ ፋሌቅ ፥ የፋሌቅ ልጅ
ወልደ ኤቦር ። የኤቦር ልጅ
ወልደ ሳላ ። የሳላ ልጅ

፴፮ ወልደ ቃይናም ።
፴፮ የቃይናም ልጅ ።
ወልደ አርፋስክድ ።
የአርፋስክድ ልጅ ።
ወልደ ሴም ። የሴም ልጅ
ወልደ ኖህ ። የኖኅ ልጅ
ወልደ ላሜህ ፥ የላሜህ ልጅ
፴፯ ወልደ ማቱሳላ ፥
፴፯ የማቱሳላ ልጅ ፥
ወልደ ሄኖክ ። የሄኖክ ልጅ
ወልደ ያሬድ ፥ የያሬድ ልጅ
ወልደ መላልኤል ።

የመላልኤል ልጅ ።
ወልደ ቃይናን ፣
የቃይናን ልጅ ።

፴፰ ወልደ ሄኖስ ።የሄኖስ ልጅ
ወልደ ሴት ። የሴት ልጅ
ወልደ አዳም ። የአዳም ልጅ
ወልደ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ልጅ ፤ እያወራረሰ መጥቶ አዳምን ወልደ እግዚአብሔር አለ ፍጥረተ እግዚአብሔር ሲል ነው ፣ አሪት ዘልደት እንዲል አዳም ዘእምእግዚአብሔር አዳም ዘእግዚአብሔር ይላል አብነት ። አንድም ወልድ ወልድ ያለ ውንለጌታ የስጡ እንደሆነ እኒህ ሁሉ አባቶች ናቸውና ። ሐተታ በምን ይመስለዋልና አዳምን ወልደ እግዚአብሔር አለው ቢሉ አዳም በኃጢአቱ ሰውን ሁሉ እንዳስጎዳ ጌታም በትሩፋቱ ሰውን ሁሉ በማጽደቁ ይመስለዋልና ። ሰባ ሰባት ትውልድ ቈጠረ ማየ አይኅ ከላይ በሰባት ዓይነት ቍልቍል ወርዷልና ከታች በሰባ ዓይነት ሽቅብ ፈልቋል ፣ በሰ፡ ሰባት ትውልድ የመጣውን ፍዳ መርገም ለማጥፋት እንደመጣ ለማጠየቅ ። ማቴዎስ ቍልቍል ሉቃስ ሽቅብ ቈጠረ የሥጋን አምላክን መሆን የአምላክን ሰው መሆን ለመናገር ። አንድም ማቴዎስ ርደቱን ሉቃስ ዕርገቱን ተናገረ ።

በእንተ ተመክሮት ዘኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወመልአ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ እግዚእ ኢየሱስ ወተመይጠ እምዮርዳኖስ ማቴ፡፬፡፩ ማር ፣ ፩ ፲፪ ።

፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ማለት የባሕርይ ልጅነቱን ከመንፈስ ቅዱስ አስመስክሮ ከዮርዳኖስ ተመለሰ ።
ወወሰዶ መንፈስ ገዳመ ።
መንፈስ ፈቃዱ ወደገዳም አወጣው ።

፪ እርብዓ መዓልተ ወእርብዓ ሌሊተ ያሜክሮ ሰይጣን ።

፪ አርባ ሌሊትና አርባ መዓልት ከሰይጣን ይፈታተን ነበር ፣
ኢበልዓ ወኢሰትየ ምንተኒ በውእቶን መዋዕል በዚያ ወራት ምንም ምን አልበላም አልጠጣም ።
ወተፈጸሞን እማንቱ መዋዕለ ርኅበ ።
አርባው ቀን ከተፈጸመ በኋላ ተራበ ።

፫ ወይቤሎ ሰይጣን እመ ወልደ እግዚአብሔር አንተ በል ከመ ዝንቱ እብን ይኩን ኅብስተ

፫ ሰይጣንም የእግዚአብሔርስ ልጅ ከሆንክ ይህ ደንጊያ እንጀራ ይሆን ዘንድ እዘዝ አለው

፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ዘዳግ፡ ፰፡ ፫፡ ማቴ፡ ፬፡፬ ።

፬ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ ጽሑፍ ዘይብል አኮ በኅብስት ከመ ዘየሐዩ ሰብእ ሰው በእንጀራ ብቻ እንዳይድን ተጽፏል። አላ በዙሉ ቃል ዘይወጽእ እምአፉሁ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር በተናገረው ነገር ሁሉ ይድናል እንጂ አለው ማቴዎስ አላ እእባን ይላል ሉቃስ ዝንቱ እብን አለ እንደ ምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ሁለት ይዞ ቀርቧል ፣ ሉቃስ አንድ ማለቱ ለመንገርከበቃ ብሎ ። አንድም ሁለት ደንጊያ ይዞ ቀርቦ አንዱን ላንተ አንዱን ለኔ ዳቦ አድርገህ እንብላ ብሎታል ዝም አለ ለኔስ ይቅርብኝ አንተ ጾንቶብሃልና ዳቦ አድርገህ ብላ ብሎታል ይህን ተካፍለው ጽፈዋል ።

፭ ወአዕረጎ ሰይጣን ውስተ ደብር ነዋህ
፭ ሰይጣን ወደረጅም ተራራ አወጣው ።
ወአርአዮ መንግሥታተ ዙሉዓለም ከመ ወኢምንትኒ፡ የዓለሙን ሁሉ ግዛት በዓይነት ቅጽበት አሳየው።

፮ ወይቤሎ ሰይጣን ዘንተ ዙሉ ምዙናነ ለከ እሁበከ ።

፮ ይህን ሁሉ ግዛት ላንተ እሰጥሃለሁ ።
ወዘንተኒ ክብረ ። ፤
ይህንም ክብር ።
እስመ ሊተ ተውህበ ፤
ለኔ ተሰጥቷልና ፤
ወለዘፈቀድኩ እሁቦ ።
እኔ ለወደድኩት እሰጠዋለሁ ።

፯ ወእምከመ ሰገድከ ሊተ አንተ ቅድሜየ ለከ ይኩንከ ኵሉ ።

፯ ለኔ ብትሰግድልኝ ሁሉም ላንተ ይሆንል ሃል አለው ።

፰ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ። ዘዳግ ፮ ፡ ፲፫ ፲ ፡ ፳ ።

፰ ጌታም መለሰ ፤
ወይቤሎ ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን ።
ሰይጣን ወግድ ከኋላየ ።
ጽሑፍ ለእግዚአብሔር አምላክከ ትስግድ ።
ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ትስግድ ዘንድ ።
ወኪያሁ ባሕቲቶ ታምልክ ።
እሱንም ብቻ ታመልክ ዘንድ ትጽፏል አለው ።
፱ ወወሰዶ ኢየሩሳሌም ።
፱ ወደ ኢየሩሳሌም አወጣው ።
ዲበ ርእሰ ማዕዘንተ ቤተ መቅደስ ።
ከምዙራብ ምሕዋሩ ጫፍ አቆመው ።

ወይቤሉ እመሰ ወልደ እግዚአብሔር አንተ ረድ
ለሊከ እምዝየ ወተወረዉ ።
የእግዚአብሔርስ ልጅ ከሆንኽ ራስህን ከዚህ ወደ
ታች ወርውር ።

፲ እስመ ጽሑፍ ዘይብል ከመ ለመላእክቲሁ ይኤዝዞሙ በእንቲአከ ከመ ይዕቀቡከ ። መዝ.፺ ፡ ፲፩

፲ ይጠብቁህ ዘንድ ስላንተ መላእክትን እንዲያዛቸው ተጽፏልና ።

፲፩ ወበእደዊሆሙ ያነሥኡከ ።
፲፩ በእጃቸው ያነሡሃል ።
ከመ ኢትትዓቀፍ በእብን እግርከ ።
እግርህ በደንጊያ እንዳይሰናከል ።

፲፪ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፲፪ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ ጽሑፍ ዘይብል ኢታመክሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ። ዘዳ.፮ ፡ ፲፮
አምላክህን አትፈታተነው ተብሏል አለው ። ሐተታ ማቴዎስ ተራራን በመጨረሻ ያደርጋል ፤ ሉቃስ ቤተ መቅደስን በመጨረሻ አደረገ ፤ አንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ተራራ ነው መጨረሻ ሉቃስ ቤተ መቅደስን መጨረሻ ማድረጉ ኀበሂ ዓርገ ወኀበሂ ነበረ ወኀበሂ መሐረ እንዲል ። ከሁሉ ይልቅ ሉቃስ ተራ ያቀናል ይባላልና የተራራ ነገር አንድ ወገን ይሁን ብሎ ቤተ መቅደስን መጨረሻ አደረገ እንጂ ፤ ይህስ በምን ይታወቃል ቢሉ ሑር እምድኅሬየ ያለው በተራራ ነው ከዚህ በኋላ አይመለስም ፤ ይህስ እንዳይሆን ሰይጣንና ውሻ ተመላላሽ ነው ብሎ ፤ ትራፍ አንተ ትቄንጽ እንዲል ፤ ከሁሉ ይልቅ የትዕቢት ጾር ይጸናል ቅዱሳንም ከበቁ በኋላ በትዕቢታቸው ይዋረዳሉ የትዕቢት ጾር ሳይቀር እሶ ፋሁላችሁ ለማሰት ቤተ መቅደስን መጨረሻ አያረገ ።

፲፫ ወፈጺሞ ሰይጣን አመክሮተ በኵሉ ኃይሉ ኀደጎ እስከ ጊዜሁ ።

፲፫ ሰይጣን በሁሉ ከተፈታተነው በኋላ እስከ ጊዜው ተወው ።
በዕለተ ዓርብ በአይሁድ ሥጋው ሁኖ እስኪያስቅለው አይደርስበትም ።
ዘከመእኀዘ ኢየሱስ ይልብከ በገሊላ ።

፲፬ ወተመይጠ እግዚእ ኢየሱስ በኃይለ መንፈስ ቅዱስ ወሖረ ገሊላ ። ማቴ. ፬ ፡ ፲፪ ማር ፩ ፡ ፲

፲፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ድል ነሥቶ ወደ ገሊላ ተመለሰ ።
ወተሰምዓ ነገሩ ውስተ ኵሉ በሐውርት ።
ትእምራቱም በየሀገሩ ተሰማ ።

፲፭ ወይሜህሮሙ በኵሉ ምኵራባቲሆሙ ።
፲፭ በየጉባኤያቸውም ያስተምራቸው ነበር ።
ወያነከሩ ምሕሮቶ ።
ትምርቱንም ያደንቁ ነበር ።

ወይሴብሕዎ ፤	አመስገኑት
ወኵሉ ያከብሮ ፤	ሁሉ ያከብረዋል ።

ዘከመ ሰበከ ኢየሱስ በናዝሬት

፲፮ ወሖረ ናዝሬት ኀበ ተሐፅነ ። ማቴ.፲፫ ፡ ፶፬ ማር.፮ ፡ ፩ ዮሐ. ፬ ፡ ፵፫

፲፮ ወዳደገበት ወደ ናዝሬት ሄደ ወቦአ ምኵራበ በዕለተ ሰንበት በከመ ያለምዱ ።
እንዳለመደ ቀዳሜ ወደምኵራብ ገባ ።

ወተንሥአ ያንብብ ፤	ሊያነብ ተነሣ ።

፲፯ ወወሀብዎ መጽሐፈ ኢሳይያስ ። ማቴ. ፲፫ ፡ ፶፬ ማር.፮ ፡ ፩ ዮሐ. ፬ ፡ ፵፫

፲፯ መጽሐፈ ኢሳይያስ ሰጡት ። አንድም አንብብ ብለው መጽሐፈ ኢሳይያስ ሰጡት ሊያነብ ተነሣ ።

፲፰ ወከሚቶ መጽሐፈ ረከበ መካነ ኀበ ጽሑፍ ዘይብል መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌየ ዘበእንቲአሁ ቀብዐኒ ። ኢሳ.፷፩ ፡ ፩

፲፰ ወደፊት እዜንዎሙ ብሎ የሚያመጣውን ዘበእንቲአሁ ብሎ አጸፈ መጽሐፉን ገልጾ ሳለ ማስተማር በኔ ህልው ና ባለ መንፈስ ቅዱስ ያዋሐደኝ እግዚአብሔር እዜንዎሙ ለነዳያን ፈነወኒ ፤ ነዳያንን አበተምራቸው ዘንድ ሳከኝ ከሚልአንቀጽ ደረሰ እንድምመንፈሰዘዚአየበሀላዌ ለሊሁ ኃደረ ላዕሌየ ብሎ ሳዊሮስ ዘእንጾኪያ ተርጉሞታልና ብሎ የባሕርይ ሕይወቴ መንፈስ ቅዱስ በኔ ህልው ነው ፤ ወዘ በእንቲአሁ ቀብዐኒ ስለ ማስተማርም ያዋሐደኝ መንፈስ ቅዱስ ነዳያንን አስተምራቸው ዘንድ ላከኝ የሚል አንቀጽ አገኘ ከሚል አንቀጽ ደረሰ ።

፲፱ እሰብክ ሎሙ ግዕዛነ ለፂውዋን ።
፲፱ የሥጋ ምርኮኞችን በተእምራት የነፍስ ምርኮኞችን በትምህርት አስተምር ዘንድ ።
ወእስተፍሥሖሙ ለኅዙናን ።
ኅዙናን ሥጋን በተእምራት ኅዙናን ነፍስን በትምህርት ደስ አሰኛቸው ዘንድ ።
ወእንግሮሙ ለግፉዓን ።
በሥጋ የተጠቁትን በተእምራት በነፍስ የተጠቁትን በትምህርት አደናቸው ዘንድ ።
እፍትሖሙ ለሙቁሓን ።
በሥጋ የታሰሩትን በተእምራት በነፍስ የታሰሩትን በትምህርት እፈታቸው ዘንድ ።
ወእፈውሶሙ ለቁሱላን ።

ቁሱላን ሥጋን በተአምራት ቁሱላን ነፍስን በትምህርት አድናቸው ዘንድ ።
ወእስብክ ሎሙ ዓመተ እግዚአብሔር ኅሪተ ።
በተመረጸች በእግዚአብሔር ቀን ማለት ምስት ዓመት ወዘኮን መዋዕለ ።
ምስቱን ወር እስተምር ዘንድ ፤ እንድም ዘመነ ሥጋዌን ወዘኮነ መዋዕለ ፤ መዋዕለ ንስሐን እስተምር ዘንድ ሾመኝ የሚል አንቀጽ አገኘ ከሚል አንቀጽ ደረሰ ።

፳ ወከደኖ መጽሐፈ ወመጠዎ ለላእክ ወነበረ ።
፳ መጽሐፉን አጥፎ ስቃቤቱ ሰጥቶት ተቀመጠ
ወእንሥኡ አዕይንቲሆሙ ኵሎሙ እለ ሀለዉ ውስተ ምኵራብ ወነጸርዎ ።
በምኵራብ ያሉ ሁሉ ዓይናቸውን አቅንተው አዩት ።

፳፩ ወአኃዘ ይቤሎሙ ዮም በጽሐ ቃለ ዝንቱ መጽሐፍ ወተሰልጠ ውስተ እዘኒከሙ ።

፳፩ የዚህ መጽሐፍ ነገር ገና ዛሬ በጆሯችሁ ደረሰ ተፈጸመ እያለ ይነግራቸው ጀመረ ።
ወእኀዘ ይመስል ሎሙ ይላል ፤ እንግዲሙ እፍትሆሙ እፈውሶሙ እስተፍሥሖሙ የተባልኩ እኔ ነኝ ግፉዓን ሙቁሓን ቍሱላን ኅዙናን የተባላችሁ እናንተ [illegible] እያለ እየመሰለ ያስተምራቸው ጀመረ

፳፪ ወኵሎሙ [illegible] ወአንከርዎ ሞገሰ ቃሉ ወማዕምን አፉሁ ።
፳፪ የተከናወነ ቃሉን ግልጥ [illegible] ናውና መናገሩን ሰምተው አደነቁ ።
ወይቤሉ አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልደ ዮሴፍ ።
ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን አሉ ።

፳፫ ወይቤሎሙ ቦኑ ትብሉኒ ዛተ ምሳሌ ዓቃቤ ሥራይ ፈውስ ርእሰከ ።

፳፫ እስኪ በውኑ ባለመድኃኒት ራስክን አድን ትሉኛላችሁ ፤ እንድም ራስህን ቤተ እስራኤልን አድን ትሉኛላችሁ ፤ እንድም ረድ እስኩ እመበቀልከ ትሉኛላችሁ ።
ኵሎ ዘሰማዕነ ዘገበርከ በቅፍርናሆም ግበር በዝየኒ በሀገርከ ፤ በቅፍርናሆም የሠራኸውን እንደሰማነው በዚህም በሀገርህ አድርግ ትሉኛላችሁ አላቸው ።

፳፬ ወይቤሎሙ አማን እብለክሙ ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ።

፳፬ ነቢይ በሀገሩ አይከብርም ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፳፭ አማን እብለክሙ ብዙኃት መበለታት ሀለዋ በውስተ እስራኤል በመዋዕለ ኤልያስ ነቢይ አመ ተዐፅወ ሰማይ ፫ተ ዓመተ ወ፮ተ አውራኀ እስከ ኮነ ረኃብ ዓቢይ ውስተ ኵሉ ምድር ።
፫ ነገሥት ፲፯ ፡ ፱

፳፭ [illegible] [illegible] ሁሉ ረኃብ ጸንቶባቸው ድርቅ [illegible] በተዘጋ ጊዜ ማለት ዝናም ለዘር ጠፍቶ ለመከር እንዳይሰጥ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ በተከለከለ ጊዜ በነቢዩ በኤልያስ ዘመን ብዙ ባልቴቶች እንደ ነበሩ ።

፳፮ ወኢ ተፈነወ ኤልያስ ኀበ አሐቲ እምኔሆን
፫ ፡ ነገ. ፲፯ ፡ ፱

፳፮ ኤልያስም ከዓቸው ወደአንዲቱ እንዳልተላከ፥ ዘእንበለ ብእሲት መበለት ዘሀለወት በሰራጵታ ዘሲዶና ።
በሲዶና ክፍል በሰራጵታ ወዳለችው ሴት እንደ ተላከ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ።

፳፯ ወብዙኃን እለ ለምጽ ሀለዉ በውስተ እስራኤል አመ መዋዕለ ኤልሳዕ ነቢይ ።

፳፯ በኤልሳዕ ዘመን በእስራኤል ዘንድ ብዙ ለምጻሞች ነበሩ ።
ወኢ ነጽሐ አሐዱሂ እምኔሆሙ ዘእንበለ ንዕማን ሶርያዊ ከሶርያዊ ሰው ከንዕማን በቀር ከሳቸው አንዱ ስንኳ አልነጻም ።

፳፰ ወተምዑ ኵሎሙ እለ ሀለዉ በምኵራብ ሰሚዖሙ ዘንተ ።

፳፰ በጉባኤ ያሉ ሁሉ ይህን ሁሉ ሰምተው ተቆጡ ። ሐተታ አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልደ ዮሴፍ ቢሉት ቦኑ ትብሉኒ ዘልክሙ ዛተ ምሳሌ ዓቃቤ ሥራይ ፈውስ ርእሰከ ብሎ አማን አማን እብለክሙ ኢይትከበር ነቢይ በሀገሩ ይላቸዋል ፤ እንድናከብርህስ ኵሎ ዘሰማዕነ ዘገበርከ በቅፍርናሆም ግበር በዝየኒ በሀገርከ ይሉታል ።
አማን እብለክሙ ብዙኃት መበለታት ወብዙኃን እለ ለምጽ ይላቸዋል ፤ እንድም አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልደ ዮሴፍ ቢሉት አማን እብለክሙ ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ብሎ ቦኑ ትብሉኒ ዛተ ምሳሌ ፤ ዓቃቤ ሥራይ ፈውስ ርእሰከ ይላቸዋል እላቸውም ኵሎ ዘሰማዕነ ዘገበርከ በቅፍርናሆም ይሉታል እማን እብለክሙ ብዙኃት መበለታት ሀለዋ ወብዙኃን እለ ለምጽ ሀለዉ ይላቸዋል ፤ እንድም አማን እብለክሙ ብዙኃት መበለታት ሀለዋ ወኢተፈነወ ኀበ አሐቲ እምኔሆን ፤ ወብዙኃን እለ ለምጽ ሀለዉ ወኢነጽሐ አሐዱሂ ዘእንበለ ንዕማን ቢላቸው ። ወተምዑ ኵሎሙ እለ ሀለዉ በምኵራብ ሰሚዖሙ ዘንተ ።
ዛሬስ በሴት በለምጻም ይመስለን ጀመረ ብለው ተቆጥተው ፤
አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልደ ዮሴፍ ይሉታል ፤ ቦኑ ትብሉኒ ዛተ ምሳሌ ዓቃቤ ሥራይ ፈውስ ርእሰከ ይላቸዋል ፤ ኵሎ ዘገበርከ በቅፍርናሆም ግበር በዝየኒ ይሉታል ፤ አማን እብለክሙ ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ብሎ ይጨርሳል ።

፳፱ ወተንሥኡ ሶቤሃ ወአውፅእዎ እፍአ እም ሀገር ።

፳፱ ፈጥነው ተነሥተው ከከተማ ወደ ዐደባባይ አወጡት ።
ወወሰድዎ ውስተ ሕፅን ርእስ ደብር ዘተነድቀት ላዕሌሁ ሀገሮሙ ከመ ያጽድፍዎ ።
ገፍተው ይጥሉት ዘንድ ከተማቸው በቆናችበት መንደራቸው በታነጸበት በታላቁ ተራራ ራስ በታች ወዳለች ወደ ታናሹ ተራራ ይዘውት ወጡ ፤ እንድም ውስተ ርእሰ ሕፅን ደብር ይላል ፤ ከታላቁ ተራራ በታች ወዳለች ወደታናሹ ተራራ በታች ወዳለች ወደታናሹ ተራራ ራስ ይዘውት ወጡ ።

፴ ወውእቱሰ ኃለፈ እንተ ማዕከሎሙ ወሖረ ።

፴ እሱ ግን በመካከላቸው አልፎ ሄደ ከረቂቅ መለኮት ጋራ እንደ ተዋሐደ ለማጠየቅ ።

ዘከመ ኃደጋ ኢየሱስ ለናዝሬት ወዘከመ ሖረ ቅፍርናሆም ።

፴፩ ወወረደ ቅፍርናሆም ሀገረ ገሊላ ።
ማቴ ፬ ፡ ፲፫ ማር ፩ ፡ ፳፩

፴፩ ገሊላ ወደሚባል አገር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ ።
ወመሐሮሙ በሰንበት ።
በሰንበት ያስተምራቸው ነበር ።

፴፪ ወያነክሩ ምሕሮቶ ።

፴፪ ትምህርቱንም ያደንቁ ነበር ።
እስመ በትእዛዝ ውእቱ ቃሉ ። ነገሩ በትእዛዝ ነበርና ።

ዘከመ አሕየወ ኢየሱስ ዘቦቱ ጋኔን ።

፴፫ ወሀሎ ፩ ብእሲ በምኵራብ ዘጋኔን እኩይ ላዕሌሁ ። ማቴ፡፯ ፡ ፳፰ ማር ፩ ፡ ፳፫

፴፫ ቢስ ጋኔን ያደረበት ሰው በጉባኤ ነበር ።

፴፬ ወከልሐ በዓቢይ ቃል ወይቤ ምንት ብየ ምስሌከ ኢየሱስ ናዝራዊ ።

፴፬ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ በኛና ባንተ መካከል ምን አለ ።
መጻእከኑ ታጥፍአነ ።
ልታጠፋን መጣህ ።
አእመርከ መኑ አንተ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ቅዱስ ሆይ ማንም እንደሆንክ ለይቼ ዐውቅሁ ብሎ አሰምቶ ተናገረ ።

፴፭ ወገሠጾ እግዚእ ኢየሱስ ።

፴፭ ጌታም ገሠጸው ።
ወይቤሎ ተፈጸም ወፃእ እምኔሁ ።
ዝም ብለህ ውጣ ከእሱ ።
ወነጸሮ ጋኔን ማእከለ ምኵራብ ። ጋኔኑ በጉባኤ [illegible]
ወወፅአ እምኔሁ ። ከእሱም ወጣ
ወኢነከዮ ወኢምንተ ።
ምንም ምን አላገኘውም ።

፴፮ ወደንገፁ ኵሎሙ ወተናገሩ በበይናቲሆሙ

፴፮ ሁሉም ደንግጠው እርስ በሳቸው ተነጋገሩ
ወይቤሉ ምንትኑ ዝንቱ ነገር ።
ይህ ነገር ምንድነው አሉ ።
እስመ በትእዛዝ ወበኃይል ይኤዝዞሙ ለአጋንንት እኩያን ወይወፅኡ ።
ክፉ አጋንንትን በኃይል በትእዛዝ ያዛቸዋል እነሱም ይወጣሉና ።

፴፯ ወወፅአ ዜናሁ ወተሰምዓ ነገሩ ውስተ ኵሉ በሐውርት እድያም ።

፴፯ የተአምራቱ ወሬ በዙሪያው አገር ስፍራ ሁሉ ወጣ ።

ዘከመ አሕየዋ ኢየሱስ ለሐማተ ጴጥሮስ ወለካልዓን ሕሙማን ።

፴፰ ወወፅአ እምኵራብ ቦአ ቤተ ስምዖን ።
ማቴ ፰ ፡ ፲፬ ማር ፩ ፡ ፴

፴፰ ከምኵራብ ወጥቶ ከስምዖን ቤት ገባ ።
ወሐማቱ ለስምዖን ተሐምም ዓቢየ ፈጸንተ ።
የስምዖን የሚስቱ እናት ብርቱ ንዳድ ታማ ነበር ።
ወነገርዎ ወሰአልዎ በእንቲአሃ ። ስለሷም ለመኑት ።

፴፱ ወቆመ ኀቤሃ ወገሠጾ ለፈጸንታ ።

፴፱ ባጠገቧም ቆሞ ደዌውን ገሠጸው ።
ወኃደጋ ፤ ተዋት ።
ወተንሥአት ሶቤሃ ወተልእከቶሙ ።
እሷም ፈጥና ተነሥታ አገለገለቻቸው ።

፵ ወሶበ የዐርብ ፀሐይ አምጽኡ ኀቤሁ ኵሎሙ ድዉያነ ወሕሙማነ ደዌ ዘዘዚአሁ ።

፵ በመሸም ጊዜ ልዩ ልዩ ደዌ ያለባቸውን ወደሱ አመጧቸው ።
ወእለ ፩ዱ አንበረ እዴሁ ላዕሌሆሙ ወፈወሶሙ ።
እሱም በየአንዳንዱ እጁን እየጫነ ፈወሳቸው ።

፵፩ ወብዙኃን አጋንንት ይወፅኡ ወይኬልሑ ።
ማር ፩ ፡ ፴፬

፵፩ ብዙ አጋንንትም እየጮሁ ይወጡ ነበር ።
ወይብልዎ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ።
የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህ አሉት ።
ወይጌሥጾሙ ወኢያብሖሙ ይንብቡ በእንተ ።
እሱም ይቆጣቸው ነበር ይናገሩ ዘንድ አልተዋቸውም ።
እስመ አእመርዎ ከመ ውእቱ ክርስቶስ ።
ክርስቶስ እንደሆነ አውቀዋልና ።

፵፪ ወጸቢሖ ወፅአ ወሖረ [illegible]

፵፪ በነጋም ጊዜ ወጥቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ [illegible]
ወኃሠሥዎ ሕዝብ ወሖሩ ኀቤሁ ።
ሕዝቡም ሁሉ ፈለጉት ወደሱም መጡ ።
[illegible]

ሊቃፋቸው እንዳይሄድ ይዘው አቆሙት ።

፵፫ ወይቤሎሙ ለካልኣትኒ አህጉር ሀለወኒ እዜንዎን በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፵፫ ለሌሎችም አገሮች የእግዚአብሔርን መንግሥት ነገር ላስተምራቸው ይገባኛል ።
[illegible] ተፈኖኩ ።
[illegible] ታልኩአለሁና ።

፵፬ ወይሰብክ በምኵራባተ ገሊላ ዘንተ ኵሎ ።

፵፬ በገሊላ ሳለ በምኵራቦችም ያስተምር ነበር።

[illegible] አኅዘ በተአምር ብዙኃን ዓመ ።

ምዕራፍ ፭

፩ ወሀለዉ ኀቤሁ ሰብእ ብዙኃን ።
፩ ብዙ ሰዎችም ከሱ ዘንድ ነበሩ ።
[illegible] ቃለ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርንም ቃል ይሰሙ ነበር ።
ወውእቱሰ ይቀውም መንገለ ሐይቀ ባሕረ ጌንሴሬጥ ።
እሱም በጌንሴሬጥ ባሕር ወደብ አጠገብ ቆሞ ነበር ።

፪ [illegible]
[illegible] ።
[illegible]
[illegible] ።
ነገር [illegible] መረባቸውን ሊያጥቡ ከመርከቦች [illegible] ነበር ።
[illegible] ውስተ አሐቲ ሐመር እምኔሆን ።
[illegible]
[illegible] አንተ ስምዖን [illegible]
ያችም የስምዖን ናት [illegible]

፫ ወይቤሎ ከመ ያርኅቃ ሕቀ እምነ ምድር [illegible] ወይምሀር ።

፫ ከምድር ጥቂት ራቅ ያደርጋት ዘንድ ግዳ [illegible] ። ሐይቃ ጌታ የተቀመጠበት የጽድቅ የወንጌል ፡ ያልተቀመጠበት የአሪት የኃጢአት [illegible]
[illegible] ተቀምጦ ሕዝቡን አስተማራቸው ።
[illegible]
[illegible] ስምዖን ይእቲ [illegible] ባሕር ወደውርድዎ መሣግሪሆሙ ።

፬ [illegible] ከፈጸመ በኋላ ስምዖንን መረባ [illegible] ወደ ባሕር ጣሉ አለው [illegible]
[illegible] ስምዖን [illegible]
[illegible]

ወይቤሎ ሊቅ ሠራሕነ ኵላ ሌሊተ እንዘ ናወርድ መሣግሪነ ።
መምህር ሆይ መረባችንን ስንጥል ሌሊቱን ሁሉ ደከምን ።
ወአልቦ ዘአኀዝነ ። ያገኘነው የለም ።
ወባሕቱ እመሰ አዘዝከ ናወርድ መሣግሪነ ።
አንተ ግን ብታዘን አይሆንም አንልም አለው ።
ፍቅረ ቢጽን ትሕትናን አስተምሯቸው ነበርና ።

፮ ወገቢሮሙ ከማሁ ትአኀዙ ብዙኃት ዓሣት ሬድፍደ ።

፮ መረባቸውንም ባወረዱ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣት ተያዙ ።
እስከ ይትበተክ መሣግሪሆሙ ።
መረባቸው እስኪቀረጥ ድረስ ።

፯ ወጸውእዎሙ ለቢጾሙ እለ ውስቴ ካልዕ ሐመር ከመ ይምጽኡ ይርድእዎሙ ።

፯ በሌላ መርከብ ያሉ ወንድሞቻቸውን አዋጡን ርዱን ብለው ጠሯቸው ።
ወመጽኡ ወመልኡ ክልኤሆን አሕማረ ።
መጥተው ሁለቱን መርከብ መሉ
እስከ ይሠጥማ ።
መርከቦቹ እስኪ [illegible]

፰ ወርእዮ ስምዖን ጴጥሮስ አስተብረከ ወሰ [illegible] እግዚእ ኢየሱስ ።

፰ ስምዖን ጴጥሮስ ይህን ባየ ጊዜ ከጌታ ጉልበት ወድቆ ሰገደ ።
ወይቤሎ ኅድገኒ አስተበቍዓከ እግዚእ ።
አቤቱ ታሰናብተኝ ዘንድ እማልድሃለሁ ።
ወሑር እምኔየ ።
ከኔ ራቅ ።
እስመ ብእሲ ኃጥእ አነ ።
ካንተ ጋራ መኖር የማይገባኝ ኃጥእ ነኝና ።

በእንተ ተጸውዖቶሙ ለሐዋርያት ቀዳማውያን ።

፱ እስመ አኃዞ ድንጋጼ ወፍርሀት ።
፱ ድንጋጤ አድሮበታልና ። ሐይቃ በባሕር ያለውን መርምሮ ያወቀ ኃጢአቱን መርምሮ ዐውቆ እንደምን ይፈርድብኝ ይሆን ብሎ ።
ወኵሎሙ እለ ምስሌሁ ደንገፁ በእንተ ዓሣት ዘተሠግሩ ።
ከሱ ጋራም የነበሩት ሁሉ በሉታያዙ ዓሣት ደንግጠው ነበር ።

፲ ወከማሁ ያዕቆብኒ ወዮሐንስ ደቂቀ ዘብዴዎስ እለ ኮኑ ሱታፌሁ [illegible]

፲ የስምዖን ወዳጆቹ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም እንዲሁ ደንግጠው ነበር ።
ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ለስምዖን ኢትፍራህ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዖንን አትፍራ እይዞህ
እምይእዜሰ ሰብአ ታሤግር ።
ከእንግዲህስ ወዲህ ሰውየምታጠምድ የምታስተምር ትሆናለህ አለው ።

፲፩ ወአውፅኡ አሕማሪሆሙ ውስተ ምድር ።
፲፩ መርከቦቻቸውን ከየብስ አውጥተው ።
ወኃደጉ ኵሎ ወተለውዎ ።
ሁሉን ትተው ለጊዜው በእግር ተከትለውት ፍጻሜው በግብር መስሉት ማቴዎስ ከባሕር ተጠሩ ያላል ሉቃስ ከወደብ ተጠሩ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ሉቃስ እንዲህ ማለቱ ወደቡ አያይዞ ከባሕር የሚያደርስ ስለሆነ ፤ እንድም ነገር እንደ ሉቃስ ነው ከወደብ ተጠርተዋል ወወዓሉ ኀቤሁ እስከ ዐሥርቱ ሰዓት እንዲል ሲማሩ ውለው ተመልሰዋል ሁለተኛ እንደ ማቴዎስ ከባሕር ተጠርተዋል የፊተኛውን ሉቃስ የኋለኛውን ማቴዎስ ጻፉ ነገር እንደ ሉቃስ ነው ፤ ጌታ ያልተቀመጠባት መርከብ የኦሪት የኃጢአት ፤ ጌታ የተቀመጠባት መርከብ የጽድቅ የወንጌል ምሳሌ ።

ዘከመ አሕየዎሙ ኢየሱስ ለለምጻዊ ወለመጻጕዕ።

፲፪ ወኮነ እንዘ ሀሎ ውስተ አሐቲ ሀገር መጽአ ብእሲ ዘለምጽ ኵለንታሁ ማቴ. ፰፥፪ ማር. ፩ ፥ ፵።

፲፪ ባንድ አገር ተቀምጦ ሳለ ሁለንተናውን ለምጽ የያዘው ሰው መጣ ።
ወሶበ ርእዮ ለእግዚእ ኢየሱስ ሰገደ በገጹ ወአስተብቍዖ ።
ጌታን ባየው ጊዜም ግንባሩን መሬት አስነክቶ ማለደው ።
ወይቤሎ እግዚኦ እመሰ ፈቀድከ ትክል አንጽሖትየ ።
አቤቱ ከወደድከስ እኔን ማዳን ይቻልሃል አለው ።

፲፫ ወሰፍሐ እዴሁ ወገሠሦ ።
፲፫ እጁን ዘርግቶ ዳሰሰው ።
ወይቤሎ እፈቅድ ንጻሕ ።
መዳንህን እውዳለሁ ዳን አለው ።
ወኃደጎ ለምጹ ሶቤሃ ።
ያን ጊዜውንም የለምጹ ደዌ ትወው ።

፲፬ ወአዘዞ መኑሂ ኢይንግር ወኢለመኑሂ ወይቤሎ ሑር እፍትን ርእሰከ ለካህን ዘሌ.፲፬.፩ ።

፲፬ ራስህን ለካህን አስመርምር ።
ወአብእ መባአ በእንተ ዘንጻሕከ በከመ አዘዘ ሙሴ ።
ከለምጽሕ ስለ ዳንክ ሙሴ እንዳዘዘ መባሕን ስጥ እንጂ ለማንም ለማን አትናገር አለው ። ከመ ይኩን ስምዓ ላዕሌሆሙ ምስክር ሊሆንባቸው ።

፲፭ ወተሰምዓ ነገሩ ፈድፋደ ።
፲፭ ነገሩም ፈጽሞ ተሰማ ።
ወመጽኡ ኀቤሁ ብዙኃን ሰብእ ይስምዕዎ ።
ብዙ ሰዎችም ሊሰሙት ወደሱ መጡ ።
ወይትፈወሱ እምደዌሆሙ ።
ከደዌያቸውም ይፈወሱ ዘንድ ።

፲፮ ወውእቱሰ ይወፅእ ገዳመ ወይጼሊ በህየ ።
፲፮ እሱ ግን ወደ ገዳም ወጥቶ ይጸልይ ነበር ።

፲፯ ወእምዝ ኮነ በአሐቲ ዕለት እመዋዕል እንዘ ሀሎ ይሜህሮሙ ወይነብሩ ፈሪሳውያን ወሊቃናተ ኦሪት እለ መጽኡ እምገሊላ ወእምኵሉ አህጉረ ይሁዳ ወእምኢየሩሳሌም ።

፲፯ ከዕለታትም ባንድ ቀን ከኢየሩሳሌምና ከገሊላ ከየሀገሩም ሁሉ የመጡ የኦሪት መምህራንና ፈሪሳውያን ከዚያ ተቀምጠው ሳሉ ያስተምር ነበር ።
ወኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ በዘይፈውስ ።
በሚፈውሳቸውም ገንዘብ ይፈውሳቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ኃይል ነበር ።

፲፰ ወአምጽኡ ኀቤሁ ብእሴ መፃጕዓ እንዘ ይጸውርዎ ፬ቱ ዕደው በዓራት ። ማቴ.፱ ፥ ፪ ማር.፪፥፫፡

፲፰ አንድ ሽባ አራት ሰዎች ባልጋ ተሸክመው አመጡት ።
ወፈቀዱ ያብእዎ ኀቤሁ ይፈውሶ ።
ሊያድነው ወደሱ ያቀርቡት ዘንድ ወደዱ ።

፲፱ ወኃጥኡ እንተ ኀበ ያበውእዎ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ እስመ ጽድቅ ሰብእ ።

፲፱ ሰው ስለበዛ እንደሚያገቡት አጡ ።
ወዓርጉ ናሕሰ ወነሠቱ ጠፈረ ወአውረድዎ ምስለ ዓራት ውስተ ቤት ።
ከሰገነት ላይ ወጥተው ጠፈሩን አፍርሰው ከናልጋው አውርደው ከቤት አገቡት ።
ቅድሜሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታ ካለበት ።

፳ ወርእዮ ሃይማኖቶሙ ወይቤሎ ለውእቱ ብእሲ ድውይ ትኃደግ ለከ ኃጢአትከ ።

፳ ሃይማኖታቸውን አይቶ ያንን የታመመ ሰው ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል አለው ።

፳፩ ወአንዘ የኀልዩ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ወይቤሉ ምንትኑ ዝንቱ ዘይነብብ ጽርፈተ ።

፳፩ ጸሐፍት ፈሪሳውያን አሰበው ይህ ስድብ የሚናገር ማነው መኑ ዘይክል ኃዲገ ኃጢአት ዘእንበለ ፩ እግዚአብሔር ባሕቲቱ ።
ከብቻው ካንድ እግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ማስተስረይ የሚቻለው ማነው ሲሉ ።

፳፪ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ዘይኄልዩ ወይቤሎሙ ምንተ አኩየ ተሐልዩ በልብክሙ ።

፳፪ ጌታም የሚያስቡትን አውቆባቸው በል ቦችሁ ለምን ክፉ ታስባላችሁ ።

፳፫ ምንት ይቀልል እምብሂለ ተኃደግ ለከ ኃጢአትከ ወእምብሂለ ተንሥእ ወጹር ዓራተከ ወሑር ።

፳፫ ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ከማ [illegible] ኃጢአትህ ተሰረየልህ ከማለት ማን ይቀላል [illegible] ።

፳፬ ከመ ታእምሩ ወትለብዉ ከመ ብውህ ሎቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ይኅድግ ኃጢአተ በዲበ ምድር ።

፳፬ [illegible] እንዲ [illegible] ተነሥ [illegible] ተነሥተህ [illegible] ወደ ቤትህ [illegible]

፳፭ ወተንሥአ ሶቤሃ ወነሥአ ዓራቶ ዘዲ ቤሁ ይሰክብ በቅድሜሆሙ ወአተወ ቤቶ እንዘ ይሴብሖ ለእግዚአብሔር ።

[illegible] የተኛበትን አልጋ ተሸ [illegible] በፊታቸው ሄደ ።

[illegible] ሁሉሙ ።
[illegible] ደንገፁ ።
[illegible] ለእግዚአብሔር ።
[illegible] አመሰገኑ ።
[illegible] ።
[illegible] ።
[illegible] አየን አሉ ።

[illegible] ተሐርየቱ ለሌዊ ።

፳፯ [illegible] ወሐለፈ እምህየ ርእየ ብእሴ መጸ [illegible] እንዘ ይነብር ኀበ ምጽባሕ ማቴ [illegible] ።
[illegible] ከዚያ ወጥቶ ሲሄድ ሌዊ የሚ [illegible] ተቀምጦ አየ ።
[illegible] ።

[illegible] ወተለዎ ።
[illegible] ትቶ ተከተለው ።
[illegible] ኀቤየ ምሳሐ በቤቱ ።
[illegible] በቤቱ ታላቅ ምሳ አቀረ [illegible]

[illegible] ብዙኃን ሰብእ ምስሌሁ መጸብሐን [illegible] ረፈቁ ምስሌሆሙ ።

ከሱ ጋራ ለምሳ የተቀመጡ ብዙ ሰዎች መጸብሐ ሐንና ኃጥአንም ነበሩ ።
ወባዕዳንኒ ብዙኃን ምስሌሆሙ ሌሎችም ብዙ ሰዎች ።

፴ ወአንጎርጐሩ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ላዕሌሁ ።

፴ ጸሐፍት ፈሪሳውያንም በሱ ተቆጡ ።
ወይቤልዎሙ ለአርዳኢሁ ለምንት ትበልዑ ወትሰ ትዩ ምስለ ኃጥአን ወመጸብሐን ።
ደቀ መዛሙርቱን ከቀራጮች ጋራ ለምን ትበላላ ችሁ ትጠጣላችሁ አሏቸው ። ሐተታ ማቴዎስ ለም ንት ይበልዕ ሊቅክሙ አሏቸው ይላል ከዚህ ሉቃስ ለምንት ትበልዑ አሏቸው አለ ። እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ መም ራችሁ ከመጸብሐን ጋራ ለምን ይበላል ብለዋቸዋል ሳይመልሱ ዝም ቢሉ እሱስ ሥርዓት ዐፍራሽ ነው እናንተ ለምን ትበላላችሁ ብለዋቸዋል ። አንድም እንደ ሉቃስ ለምን ትበላላችሁ ብለው ጠይቀዋ ቸዋል ፣ ዝም አሉ እናንተስ ዐላዋቆች ናችሁ ፣ እረ ዐዋቂ ነኝ የሚለው ያ ለምን ይበላል ብለዋቸዋል የፊተኛውን ማቴዎስ የኋለኛውን ሉቃስ ጻፉ ።

፴፩ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፴፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ሕሙማን ይፈቅዱዎ ለዓቃቤ ሥራይ ።
ባለመድኃኒትን ድውያን ይሹታል ።
ወአኮ ጥዑያን ።
ጤነኞች ግን አይሹትም ።

፴፪ ኢመጻእኩ እጸውዕ ጻድቃነ ።
፴፪ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም ።
አላ ኃጥአነ ለንስሐ ።
ኃጥአንን ወደ ንስሐ ልጠራ ነው እንጂ ።

፴፫ ወይቤልዎ ለምንት አርዳኢሁ ለዮሐንስ ጽኑዐ ይጸውሙ ።

፴፫ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱ ብዙ ይጾማሉ ።
ወጸሎተ ይገብሩ ።
ጸሎትም ይጸልያሉ ።
ወከማሁ እለሂ ፈሪሳውያን ።
እንደዚሁ የፈሪሳውያንም ደቀ መዛሙርት ይጾማሉ ።
ወአርዳኢከሰ እሊአከ ይበልዑ ወይሰትዩ ።
ያንተ ደቀ መዛሙርት ግን ለምን ይበላሉ ይጠጣሉ አሉት ።

፴፬ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢይክሉ ደቂቀ ለመርዓዊ ጸዊመ እንዘ ሀሎ መርዓዊ ምስሌ ሆሙ ።

፴፬ ሙሽራ ከነሱ ጋራ ሳለ የሙሽራ ሚዜ ዎች መጾም አይቻላቸውም ።

፴፭ ወባሕቱ ይመጽእ መዋዕል አመ ፡ ይነሥእዎ ለመርዓዊ እምኔሆሙ ።

፴፭ ነገር ግን ሙሽራው ከነሱ የሚለይበት ጊዜ ይመጣል ።
ወይእተ አሚረ ይጸውሙ ።
ያንጊዜ ይጾማሉ ።

፴፮ ወይቤሎሙ ምሳሌ ።
፴፮ በምሳሌ ነገራቸው ።
አልቦ ዘይጠቅብ ግምደ ድርግሃ ልብሰ ውስተ ስጠት ብሉይ ።
ያዲስ ልብስቁራጭ ባረጀ ልብስ የሚጠቅም የለም።
ወእመ አኮሰ ይሠጥጦ ሐዲስ ለብሉይ ።
ያለዚያ ግን አዲሱ አሮጌውን ይቀደዋል ።
ወኢየአሪ ምስለ ብሉይ ወኢይሰነአው ።
አይሰማማውም ።

፴፯ ወአልቦ ዘይወዲ ወይነ ሐዲስ ውስተ ዝቅ ብሉይ ።

፴፯ ጉሽ ጠጅ ባዲስ ራዋት የሚሾም የለም ።

ወእመ አኮሰ ዝቁሂ ይነቅዕ ። ያለዚያ ረዋቱ ይቀደዳል ወይኑሂ ይትከዓው ። ወይኑም ይፈሳል ። ወዝቁሂ ይትኃጐል ። ራዋቱም ይቀደዳል ።

፴፰ ወለወይንሰ ሐዲስ ውስተ ዝቅ ሐዲስ ይወድይዎ ።

፴፰ ጉሹን ጠጅ ግን ባዲስ ራዋት ይሾሙታል ወይትዓቀቡ በበይናቲሆሙ ።
እርስ በርሳቸውም ይጠባበቃሉ ።

፴፱ ወአልቦ ዘይስቲ ጸአፌ ሐዲስ እንዘ ይፈቅድ ከራሜ ።

፴፱ ጥሩ ጠጅ ሊጠጣ ወዶ ሳለ ጉሽ ጠጅ የሚጠጣ የለም ።
እስመ ይኄይስ ካራሚ እምሐዲስ ።
ከጉሹ ጥሩው ይሻላልና ፤ እንደዚህም ሁሉ ወንጌልን ሊማር ወዶ ሳለ ኦሪትን የሚማር የለም እስመ ይኄይስ ፤ ከኦሪት ወንጌል ትበልጣለችና ። ሐተታ ጉሽ ጠጅ አላት ኦሪትን ይህ ጉሽ ጠጅ ሲጠጡት ለጊዜው ደስ ያሰኛል ከሆድ ገብቶ አይሰማማም ሲጠጡት ደስ እንዲያሰኝ ፤ ኦሪትም ለእም ዓቀብከ ኦሪተከ ትበልዕ ከራሜ ከራሚከ ወይሰፍፍ ማኅበብተ ወይንከ ወትሬኢ ውሉደ ውሉድከ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ስትል ደስ ታሰኛለች ፤ ጉሽ ጠጅ ከሆድ ገብቶ እንዳይስማማ ኦሪትም በሞት ጊዜ ከርደተ ገሃነም አታድንም? ፤ ጥሩ ጠጅ አላት ወንጌልን ፤ ጥሩ ጠጅ ሲጠጡት ይከብዳል ይገርማል ከሆድ ከገባ በኋላ ገብቶ ይስማማል ። ወንጌልም ለዚህ ጸፍአከ መልታሕቴከ እንተ የማን ሚጥ ሎቱ ካልዕታሂ ወለዘሂ ይፈቅድ ይትዓገልከ መልበስከ ኅድግ ሎቱ ክዳንከኒ ወለዘሂ አበጠከ ፩ደ ምዕራፈ ሑር ምስሌሁ ወአብጽሕ ሎቱ ፪ኤ ምዕራፈ ስትል ትገርማለች ከሆድ ከገባ በኋላ እንዲስማማ ርደተ ገሃነም የለባትምና ።
አንድም አልቦ ዘይሰቲ ከራሜ እንዘ ይፈቅድ ጸዕፌ ።
አፍለኛውን ሊጠጣ ወዶ ሳለ መጻጻ የሚጠጣ የለም ።
እስመ ይብል ይኄይስ ሐዲስ እምነ ከራሚ ፤ ከመጻጻ አፍለኛው ይሻላል ይላል ። እንደዚሁም ሁሉ ወንጌልን ሊማር ወዶ ሳለ ኦሪትን የሚማር የለም ከኦሪት ወንጌል ትበልጣለች ይላልና ኦሪትን መጻጻ አላት አስቀድማ ተሠርታለችና ወንጌልን አፍለኛ አላት በኋላ ተሠርታለችና ።

ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ በእንተ ሰዊት ወዕለተ ሰንበት ።

ምዕራፍ ፮ ።

፩ ወእምዝ ካዕበ ወፈረ እግዚእ ኢየሱስ ማዕከለ ገራውህ በሰንበት ።

፩ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት በእርሻ መካከል ሄደ ።
ወመሐዉ አርዳኢሁ ሰዊተ ወሐሰዩ በእደዊሆሙ ወበልዑ ። ደቀ መዛሙርቱ እሸት እየቆረጡ እያሹ ይበሉ ጀመር ።

፪ ወይቤልዎሙ ፈሪሳውያን ለምንትኑ ትገብሩ ዘኢይከውን ለገቢር በሰንበት ።

፪ ፈሪሳውያን በሰንበት ለመሥራት የማይገባ ሥራ ለምን ትሠራላችሁ አሏቸው ።
ሐተታ ፤ ማቴዎስ ርኢ ዘይገብሩ አርዳኢከ ብለው ጠየቁት ይላል ። ሉቃስ ለምንት ትገብሩ አሏቸው አለ ። እንደምን ነው አይለያይም ቢሉ አይለያይም ። ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ርኢ ዘይገብሩ አርዳኢከ። ብለው ጠይቀውታል ። ዝም አላቸው ለምንት ትገብሩ ብለው እነሱን ጠይቀዋቸዋል ። የፊተኛውን ማቴዎስ የኋለኛውን ሉቃስ ጽፈዋል ። አንድም ነገር እንደ ሉቃስ ነው ፤ ለምንት ትገብሩ ብለው እነሱን ጠይቀዋቸዋል ። ዝም ቢሏቸው ባይመልሱላቸው ርኢ ዘይገብሩ ብለው እሱን ጠይቀውታል እሱ ይመልስላቸዋል ።

፫ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፫ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ኢያንበብክሙኑ ዘገብረ ዳዊት አመ ርኅበ።
ዳዊት በተራበ ጊዜ ያደረገውን አላነበባችሁምን ። ውእቱሂ እርሱም ወእለ ምስሌሁ ። ከሱም ጋራ ያሉት

፬ ዘከመ ቦአ ቤተ እግዚአብሔር ወነሥአ ኅብስተ ቍርባን ።

፬ ከቤተ እግዚአብሔር ገብቶ የሚሠሩትንመሥዋዕት እንደ ወሰደ ።
ወበልዓ ውእቱኒ ፤ እሱም እንደ በላ ። ወወሀቦሙ፡ ለእለ ምስሌሁ ዘኢይከውኖሙ ለበሊዕ ።
ከሱም ጋራ ላሉ ለመብላት የማይገባቸውን እንደ ሰጣቸው ። ዘእንበለ ለካህናት ለባሕቲቶሙ ለካህናት ብቻ ይገባቸዋል እንጂ ።

፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ውእቱ ለሰንበት ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

፭ የሰንበት ጌታዋም ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ነው አላቸው ።

ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ ለዘየብሰት እዴሁ ።

፮ ወእምዝ በካልዕት ሰንበት ቦአ ምኵራበ ወመሀሮሙ ።

፮ ከዚህ በኋላ በሁለተኛው ሰንበት ከምኵራብ ገብቶ አስተማራቸው ።

፯ ወሀሎ ብእሲ ዘየብሰት እዴሁ እንተ የማን ።
፯ ቀኝ እጁ የሰለለች ሰው ነበር ወይትዓቀብዎ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ለእመ ይፌውሶ በሰንበት ። ጸሐፍት ፈሪሳውያን በሰንበት ይፈውሰው እንደሆነ ብለው ይጠባበቁት ነበር ።
ከመ ይርከቡ ምክንያተ ዘያስተዋድይዎ ።
በሚያማልሉት ነገር ያማልሉት ዘንድ ምክንያት ያገኙበት ዘንድ ።

፰ ወውእቱሰ የአምሮሙ ዘይሔልዩ ።
፰ እሱ ግን የሚያስቡትን ያውቅባቸው ነበር ።
ወይቤሎ ለውእቱ ብእሲ ተንሥእ ወቁም ማዕከለ ።
ያንንም ሰው እለው ተነሥተህ ቁም ።
ወተንሥአ ወቆመ ።
ተነሥቶ ቆመ ።

፱ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እሴእለክሙ ወምንት ውእቱ ዘይደሉ ዘይከውን በሰንበት ።
፱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት የሚገባውን እጠይቃችኋለሁ ።
ገቢረ ሠናይኑ ፡ አው ገቢረ እኪይኑ ።
መልካም መሥራት ነው ። ወይስ ክፉ መሥራት ።
አሕይዎ ነፍስኑ። ሠሪመ ቀቲል ነፍስ ማዳን ነውን ።
ወይስ ነፍስ መግደል ነው የሚገባው አላቸው ።
፲ ወአርመመ ፤ ዝም አለ ወነጺሮ ኵሎሙ በመዓት ይቤሎ ለውእቱ ብእሲ ስፋሕ እዴከ ።
፲ እነሱንም በመዓት አይቶ እጅህን ዘርጋ አለው ወሰፍሐ ። እጁን ዘረጋ ።
ወሐይወት እዴሁ ከመ ካልእታ እንደ ግራዪቱ ሆነች
፲፩ ወእሙንቱሰ የአብዱ ፈድፋደ ።
፲፩ እነሱ ግን እጅግ ተናደዱ ።

ወተማከሩ ወበበይናቲሆሙ ዘከመ ይሬስይዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታን እንደሚያደርጉት እርስ በርሳቸው ተማከሩ ።

ዘከመ ሰመዮሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ሐዋርያት ።

፲፪ ወእምዝ ኮነ በውእቱ መዋዕል ዓርገ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ደብር ይጼሊ ።

፲፪ በዚያ ወራት ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ ።
ወያሌሊ በጸሎት ኀበ እግዚአብሔር ።
ያስተበቍዕ ሲል ነው። ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ይተጋ ዘንድ ።

፲፫ ወጸውዖሙ ለአርዳኢሁ ማቴ፡ ፲፩፡ ማር፡ ፫ ፡ ፲፫ ።

፲፫ በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራቸው።
ወኀረየ እምውስቴቶሙ ዐሥርተ ወክልኤተ ወሰመዮሙ ሐዋርያተ ።
ከነሱም ዐሥራ ሁለቱን መርጦ ሐዋርያት አላቸው
፲፬ ስምዖን ዘተሰምየ ጴጥሮስ ።
፲፬ ጴጥሮስ የተባለ ስምዖን ።
ወእንድርያስ እኁሁ ።   ወንድሙ እንድርያስ ፤
ወያዕቆብ ።   ያዕቆብም ።
ወዮሐንስ ።   ዮሐንስም
ወፊልጶስ ።   ፊልጶስም
ወበርተሎሜዎስ ።   በርተሎሜዎስም ።

፲፭ ወማቴዎስ ።   ማቴዎስም
፲፭ ወቶማስ ።   ቶማስም
ወያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ።
የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ።

፲፮ ወስምዖን ቀናዊ ።
፲፮ ቀናዊ የሚባለው ስምዖን ።
ወይሁዳ ዘያዕቆብ ።
የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ ።
ወይሁዳ አስቆሮታዊ ዘአርዎ ወዘአግብኦ ።
ከድቶ ያስያዘው የአስቆሮት ሰው ይሁዳም ናቸው ።

፲፯ ወወረደ ምስሌሆሙ ወቆመ ውስተ መካን ርሒብ ።

፲፯ ከርሳቸው ጋራም ወርዶ በሰፊ ቦታ ቆመ ።
ወብዙኃን ሰብእ እምአርዳኢሁ ።
ከደቀ መዛሙርቱም ወገን ብዙ ሰዎች ነበሩ ።
ወብዙኃን ጥቀ እምሕዝብ ፡
ከሕዝቡም ወገን እጅግ ብዙ ሰዎች ።
ዘእምኵሉ ይሁዳ ።
ከይሁዳ አውራጃ ሁሉ የመጡ ።
ወእምኢየሩሳሌም ወእምጢሮስ ወሲዶና ። ወእምጼራልዮስ ወጼራልዩ ።
ከኢየሩሳሌምና ከጼራልዮስ ።

ወእምጢሮስ ወሲዶና እለ መጽኡ ይስምዕዎ ወይትፈወሱ እምደዌሆሙ ።
ከጢሮስና ከሲዶና ሊሰሙት ከደዌያቸውም ሊፈወሱ የመጡ ።

፲፰ ወእለሂ ኢጋንንት እኩያን ፡

፲፰ የክፉዎች አጋንንት ያደሩባቸውም ይድኑ ነበር ።

፲፱ ወኵሎሙ አሕዛብ ይፈቅዱ ይግሥሥዎ ።

፲፱ ሕዝቡ ሁሉ ሊዳስሱት ይሹ ነበር ።
እስመ ኃይል ይወፅእ እምኔሁ ።
ኃይል ከሱ ትወጣ ነበርና ።
ወያሐይዎሙ ለኵሎሙ ፡
ሁሉንም ይፈውሳቸው ነበር ።

በእንተ ሰብከት በውስተ ደብር ወበእንተ ብፁዓን ።

፳ ወውእቱሰ አንሥአ አእይንቲሁ ኀበ አርዳኢሁ ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፪ ።

፳ እሱ ግን ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዓይኑን እነሣ ።
ወይቤሎሙ ብፁዓን አንትሙ ነዳያን ።
ድሆች ብፁዓን ናችሁ ።
እስመ ለክሙ ይእቲ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
መንግሥተ ሰማያት የናንተ ናትና ።

፳፩ ብፁዓን እለ ትርኅቡ ይእዜ ፡ ማቴ፡፭፡፮ ።
ዛሬ የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ ።

፳፩ እስመ ትጸግቡ ። ትጸግባላችሁና ።
ብፁዓን እለ ትበክዩ ይእዜ ።
ዛሬ የምታለቅሱ የተመሰገናችሁ ናችሁ ።
እስመ ትስሕቁ ። ደስ ይላችኋልና ።

፳፪ ብፁዓን አንትሙ ሶበ ይጸልኡክሙ ሰብእ።

፳፪ እናንተም ሰዎች ቢጠሏችሁ የተመሰገናችሁ ናችሁ ።
ወይፈልጡክሙ ። ቢለዩዋችሁ ።
ወይሰድዱክሙ ። ከሀገራችሁ ቢያሰድዷችሁ ።
ወይጼዕሉክሙ ። ቢሰድቧችሁ ።
ወያወፅኡ ለክሙ ስመ እኩየ በእንተ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
በወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ስለ አመናችሁ ክፉ ስም ቢያወጡላችሁ ።

፳፫ ተፈሥሑ ወተሐሠዩ ይእተ አሚረ ።

፳፫ በዚያን ጊዜ ደስ ይበላችሁ ።
ወእንፈርዕፁ ኃሤትም አድርጉ ።
እስመ ብዙኅ ዕሤትክሙ በሰማያት ።
ዋጋችሁ በሰማይ ብዙ ነውና ።
እስመከማሁ ረሰይዎሙ ለነቢያት ቀደምትአበዊሆሙ።
ባባቶቻቸው በነቢያት እንዲህ ያደርጉ ነበርና ።

፳፬ ወባሕቱ አሌ ለክሙ አብዕልት ።
ሲራ፡ ፴፩፡ ፰ አሞ. ፯ ፡ ፩

፳፬ እናንተ ባለጸጎች ወዮላችሁ ።
እስመ ሰለጥክሙ ትፍሥሕትክሙ ።
ሐተታ ሉቃስ አጸፋ ይጽፋል ደስታችሁን ጨርሳችኋልና ።

፳፭ አሌ ለክሙ እለ ትጸግቡ ይእዜ ። ኢሳ ፷፭ ፡ ፲፫ ።

፳፭ ዛሬ የምትጸግቡ ወዮላችሁ ።
እስመ ትርኅቡ ። ትራባላችሁና ።
አሌ ለክሙ እለ ትስሕቁ ይእዜ ።
ዛሬ የምትስቁ ወዮላችሁ ።
እስመ ትበክዩ ወትላህዉ ። ታለቅሳላችሁና ።

፳፮ አሌ ለክሙ ሶበ ሠናየ ይብሉ ሰብእ ላዕሌክሙ ወይዌድሱክሙ ።

፳፮ ሰው ቢያመሰግናችሁ ወዮላችሁ ።
እስመ ከማሁ ረሰይዎሙ ለነቢያተ ሐሰት አበዊሆሙ
ነቢያተ ሐሰት ።
አባቶቻችሁን ሰላም ሳይኖር ሰላም እያሉ በሐሰት ጉድተዋቸዋልና በሐሰት ቢያመሰግኑዋችሁ ወዮላችሁ ።
አንድም ለነቢየተ ሐሰት አበዊክሙ ሰው በውዳሴ ከንቱ ቢያመሰግናችሁ ወዮላችሁ ። ቀድሞ አባቶቻችሁን ነቢየተ ሐሰትን ሕግ መጠበቁ ሳይኖር ሕግ ጠባቆች እያሉ ጉድተዋቸዋልና ሰው በውዳሴ ከንቱ ቢያመሰግናችሁ ወዮላችሁ ። አንድም ቅጽል አድርገው ነቢየተ ሐሰት አባቶቻችሁን በሐሰት ጉድተዋቸዋልና ሰው በሐሰት ቢያመሰግናችሁ ወዮላችሁ ።

፳፯ ወለክሙሰ እለ ትሰምዑኒ እብለክሙ አፍቅሩ ጸላእተክሙ ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፬ ።

፳፯ ለምትሰሙኝ ለናንተ ግን ጠላታችሁን ውደዱ እላችኋለሁ ።
ወግበሩ ሠናየ ለእለ ይፃረሩክሙ ።
ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ ።

፳፰ ወጸጋርዎሙ ለእለ ይረግሙክሙ ።

፳፰ የሚረግሟችሁን መርቁ ።
ወጸልዩ ለእለ ይትኤገሉክሙ ።
ለሚበድሏችሁም ለምኑ ።

፳፱ ወለዘሂ ጸፍአከ መልታሕቴከ ሚጥ ሎቱ ካልዕታሂ ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፴፱ ፩ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፯ ።

፳፱ ፊትህን ለጸፋህም ሁለተኛውን መልስለት ።
ወለዘሂ ነሥአከ ፡ ልብሰከ ፡ ክዳንከኒ ኢትክልኦ ።
መጐናጸፊያህን ለመሰደብህም ቀሚስህን አትንሣው።

፴ ለኵሉ ለዘሰአለከ ሀብ ።

፴ ለለመነህ ሁሉ ስጥ ።
ወለእመሂ ሂደከ ንዋየከ ኢትክልኦ ።
የሚቀማህንም አትከልክለው ።

፴፩ ወበከመ ትፈቅዱ ይግበሩ ለክሙ ሰብእ ከማሁ ግበሩ ሎሙ አንትሙ ጦቢ ፬ ፥ ፲፭ ማቴ.፯.፲፪

፴፩ ሰው ሊያደርግላችሁ የምትወዱትን እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው ።

፴፪ ወእመሰ ዳዕሙ ዘአፍቀረክሙ አፍቀርክሙ ምንትኑ ዕሤትክሙ ።

፴፪ የወደዳችሁንም ብቻ ክወደዳችሁ ዋጋችሁ ምንድነው ።
ኃጥአንሂ ዘሰ ይገብሩ ።
ይህንስ ኃጥአንም ያደርጉታል ።

፴፫ ወእመኒ አሠነይክሙ ለእለ ያሤንዩ ለክሙ ምንትኑ እንከ ዕሤትክሙ ።

፴፫ መልካም ለሚያደርጉላችሁስ መልካም ብታደርጉ ምንድነው ዋጋችሁ ።
ኃጥአንሂ ከማሁሰ ይገብሩ ።
እንደዚህስ ኃጥአንም ያደርጋሉ ።

፴፬ ወእመኒ ለቃሕክሙ እምኀበ ዘትሴፈው ትትፈደዩ እምኔሁ ምንትኑ እንከ ዕሤትክሙ ። ዘዳግ ፲፭፥፰ ማቴ ፥ ፭ ፤ ፵፪ ።

፴፬ እንዲመልሱላችሁ ተስፋ ለምታደርጉዋቸው የምታበድሩ ከሆነ ዋጋችሁ ምንድነው ። እስመ ኃጥአንሂ ይሌቅሕዎሙ ለኃጥአን ከመ ይትፈደይዎሙ ዕሩየ ።

ያበደሩትን ሊወስዱ ኃጥአንም ለኃጥአን ያበድሩዋቸዋልና ።

፴፭ ወይእዜኒ አፍቅሩ ጸላእተክሙ ።
፴፭ አሁንም ጠላታችሁን ውደዱ ።
ወአሠንዩ ሎሙ ፤
መልካም አድርጉላቸው ፤
ወለቅሑ እንዘ ኢትሴፈው ትትፈደዩ ፤
እንከፈላለን ብላችሁ ተስፋ ሳታደርጉ አበድሩ ፤
ወይከውን ብዙኀ ዕሤትክሙ ፤
ዋጋችሁ ብዙ ይሆናልና ።
ወትከውኑ ውሉደ ልዑል ።
የልዑልም ልጅ ትሆናላችሁ ።

እስመ ውእቱ ኄር ላዕለኄራን ወላዕለ እኩያን ።
እሱ ለክፉውም ለበጎውም ቸር ነውና ።

፴፮ ወኩኑ መሐርያነ ከመ አቡክሙ ሰማያዊ መሐሪ ውእቱ ።

፴፮ ሰማያዊ አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ እናንተም የምትራሩ ሁኑ ።

፴፯ ኢትኰንኑ ። ማቴ.፯፥፩ ።
፴፯ አትዘራረፉም ።
[illegible] አትቋረሉም

ኢትግፍዑ ።	እትበድሉ ።
ወኢይግፍዑክሙ ።	አይበድሏችሁ ፤
ኀድጉ ፤	ተው ፤
ወየኀድጉ ለክሙ ፤	ይተውላችኋል ።

፴፰ ሀቡ ወይትወሀበክሙ ፤ ማቴ.፯ ፤ ፪. ማር ፬፥ ፳፬ ።

፴፰ ስጡ ይሰጣችኋል ።
መስፈርተ ሠናየ ንኅኑኃ ወምሉአ ወዝኅዙኃ ።
በመልካም መስፈርያ መልተው ፤ ንኅኑኃ ። ደርበብ አድርገው ። ምሉእ መልተው ።
ወዝኅዙኃ ጠብ ጠብ ሲል ።
ይሁቡክሙ ውስተ ሕፅንክሙ በብብታችሁ ማለት ሰውረው ይሰጧችኋል ። እንድም ሥራውን በሦስት ወገን ይሠሩታል በወጣኒነት በማእከላዊነት በፍጹምነት ክብሩንም በዚያው ልክ ይወርሱታልና ። አንድም በዚህ ዓለም በገነት አንድ ወገን በደብረ ጽዮን በመንግሥተ ሰማያት ይወርሱታልና ።
ወበመስፈርት ዘሰፈርክሙ ይሰፍሩ ለክሙ ።
በምትሰፍሩበትም መስፈርያ ይሰፍሩላችኋል ።

በእንተ ካልዓን ትእዛዛት ።

፴፱ ወመሰለ ሎሙ ።
፴፱ ምሳሌ መሰለላቸው ፤
ወይቤሎሙ ይክልኑ ዕውር ለዕውር መሪሐ ።
ዕውር ዕውርን ሊመራው ይቻለዋልን ።

፵ አኮኑ ክልኤሆሙ ይወድቁ ውስተ ግብ ፤ ማቴ.፲፥ ፳፬ ዮሐ.፲፫፥ ፲፮ ።

፵ ሁለቱ ክጉድጓድ ይወድቁ የለምን አላቸው። አንድ አርእስት አልቦ ረድዕ ዘየዓቢ እምነ ሊቁ ከመ ምህሩ የሚበልጥ ደቀ መዝሙር የለም ሁለት አርእስት ተናገረ ለሁለቱም ያመጣል ፤ መጠኑ ለኵሉ ይኩን ከመ ሊቁ ።
የሁሉም መጠኑ እንደ መምህሩ ይሁን ።

፵፩ ምንተኑ ትሬኢ ኃሠረ ዘውስተ ዓይነ ቢጽከ ። ማቴ.፯ ፥ ፫ ።

፵፩ በወንድምህ ዓይን ጉድፍ ስምን ታያለህ ። ሐተታ ዕውር ላለው ወኢትሬኢ ሠርዌ ዘውስተ ዓይንከ ።
ባንተ ዓይን ያለውን ምሰሶ አታስተውለውም ።

፵፪ ወእፎ ትብሎ ለቢጽከ ተዓገሥ እትየ አውፅእ ኃሠረ እምውስተ ዓይንከ ።

፵፪ ወንድምህን ከዓይንህ ያለውን ጉድፍ አወጣ ዘንድ ተወኝ እንደምን ትለዋለህ ።
ወአንተሰ ኢትሬኢ ሠርዌ ዘውስተ ዓይንከ ።
ባንተ ዓይን ያለውን ምሰሶ ግን አታስተውለውም ።
ወእምዝ ትሬኢ ታውፅእ ኃሠረ እምዓይነ ቢጽከ ።

ከዚህ በኋላ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ለማውጣት ትችላለህ ።

፵፫ እልቦ ዕፅ ሠናይ ዘያፈሪ ፍሬ እኩየ ፣ ማቴ ፯ ፣ ፲፰ ፲፪ ፣ ፴፫ ።

፵፫ እልቦ ረድዕ ላለው ። ክፉ ፍሬ የሚያፈራ መልካም ዕንጨት የለም ።
ወአልቦ ዕፅ እኩይ ዘይፈሪ ፍሬ ሠናየ ።
መልካም ፍሬ የሚያፈራ ክፉ ዕንጨት የለም ።

፵፬ ወኵሉ ዕፅ እምፍሬሁ ይትዓወቅ ።

፵፬ ዕንጨትም ሁሉ በፍሬው ይታወቃል ።
ወኢያዓርሩ በለስ እምዓሥዋክ ።
ከሾህ በለስን አይሰበስቡም ።
ወኢይቀስሙ እስካለ እምእሜከላ ።
ከደንደርም ወይንን አይለቅሙም ።

፵፭ ኄር ብእሲ እምሠናይ መዝገበ ልቡ ያወፅእ ለሠናይት ።

፵፭ ቸር ሰው ከቸር ልቡ መዝገብ ቸርነቱን ያወጣል ።
ወእኩይ ብእሲ እምእኩይ መዝገበ ልቡ ያወፅእ ለእኪት
ክፉ ሰው ግን ከክፉ ልቡ ሣጥን ከፉ ነገርን ያወጣል ።
እስመ እምተረፈ ልብ ይነብብ አፍ ።
አፍ ከልብ የተረፈውን ይናገራልና ።

፵፮ ለምንት ትብሉኒ እግዚእ እግዚእ ። ማቴ ፯ ፣ ፳፩ ። ሮሜ. ፪ ፣ ፲ ፣ ፫ ያዕ. ፩ ፣ ፳፪ ።

፵፮ ለምን አቤቱ አቤቱ ትሉኛላችሁ ።
ወኢትገብሩ ዘእቤለክሙ ።
የምነግራችሁን አትሠሩትም ።

፵፯ ኵሉ ዘይመጽእ ኀቤየ ይሰምዓኒ ቃልየ ወይገብሮን እርእየክሙ ዘይመስል ።

፵፯ ወደኔ የሚመጣ ነገሬን ሰምቶ የሚሠራው ሁሉ የሚመስለውን አሳያችኋለሁ ።

፵፰ ይመስል ብእሴ ጠቢበ ዘሐነጸ ቤቶ ወከረየ ወአዕመቀ ወሣረረ መሠረቶ ዲበ ኰኵሕ ።

፵፰ አጥብቆ ቆፍሮ መሠረቱን ከጭንጫ ላይ መሥርቶ ቤቱን የሚሠራን ብልህ ሰውን ይመስላል ።
ወበዝኃን አፍላግ መጺኦሙ ገፍዖ ወሐይዝት ለውእቱ ቤት ።

ብዙ ጐርፍ በፈሰሰ ጊዜ ፈሳሾች ያንን ቤት ገፉት ።
ወኢክህሉ አንቀልቅሎቶ ።
አላናወጡትም ።
እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ ።
ከጭንጫ ላይ ተመሥርቷልና ።

፵፱ ወዘሰ ይሰምዓኒ ቃልየ ወኢይገብሮ ይመስል ብእሴ ዘሐነጸ ቤቶ መልዕልተ ምድር ዘእንበለ መሠረት ።

፵፱ ቃሌን ሰምቶ የማይሠራው ግን ሳይመሠርት ቤቱን በምድር ላይ የሚሠራ ሰውን ይመስላል ።
ወገፍዖ ወሐይዝት ። ፈሳሾች ገፉት ።
ወወድቀ ሶቤሃ ። ያንጊዜውን ወደቀ ።
ወኮነ ድቀቱ ዓቢየ ። መውደቁም ታላቅ ሆነ ።

በእንተ ወዓሊ ዘመስፍን ።

ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወፈጺሞ ነጊሮቶሙ ቃሎ ለሕዝብ ቦአ ቅፍርናሆም ። ማቴ. ፰ ፣ ፭ ።

፩ ትምህርቱን ለሕዝቡ ነግሮ ከፈጸመ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ገባ ።

፪ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ መስፍን ።
፪ አንድ ሹም ነበር ።
ወገብሩ ይደዊ ። ባሪያው ታሞ ነበር ።
ወአልጸቀ ይሙት ። ሊሞት ቀርቦ ነበር ።
ወክቡር ውእቱ በኀቤሁ ። ያውም ባለሟሉ ነው ።

፫ ወሰሚዖ በእንተ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ይመጽእ ለአከ ኀቤሁ ረበናተ አይሁድ ።

፫ ጌታችን ኢየሱስ እንደ መጣ ወሬ በሰማ ጊዜም የአይሁድን ሽማግሌዎች ላከ ።
ያስተበቍዕዎ ከመ ይምጻእ ወያሕዩ ሎቱ ገብሮ ።
ባሪያውን እንዲያድንለት ይለምኑት ዘንድ ።

፬ ወመጽኡ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወአስተብቍዕዎ ።

፬ ወደ ጌታ መጥተው ለመኑት ።
ወይቤልዎ ነዓ ፍጡነ ረድ ።
ፈጥነህ ውረድ ።
እስመ ይደልዎ ትግበር ዘ ስሌሁ ዘንተ ።
ሎቱ ሲል ነው ። ግበር ምስሌሁ እንዲል ። ይህን ልታደርግለት ይገባዋልና ።

፭ እስመ ያፈቅር ሕዝበነ ።
፭ ወገኖቻችንን ይወዳልና ።
ወምኵራበነኒ ውእቱ ሐነጸ ለነ ።
እሱ የጸሎት ቤት ሰርቶልናልና ። ሐተታ ካርባ ስምንቱ ምኵራብ እንዱን ሰርቶላቸዋል ። አንድም አልፎ አልፎ የፈረሰውን መጠቀም ነው ። ማቴዎስ ወልዱ ይላል ሉቃስ ገብሩ እለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር ። እንደ ማቴዎስ ነው ልጁ ነው ሉቃስ ገብሩ እለ ክቡተ ሰብአ ወልዶ ታልና ። አንድም ሉቃስ ገብሩ ማለቱ ባለሟሉ ሲል

ነው ። ኢዮብ ገብርየ ሙሴ ገብርየ እንዲል ፤ ማቴዎስ እሱ ሄዶ ተናገረ ይላል ። ሉቃስ ረባናትን ላከ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው እሱ ሄዶ ተናግሯል ዝም ቢለው ባይመልስለት እኔንስ ዝም አለኝ እናንተ ሄዳችሁ ንገሩት ቢላቸው ሄደው ተናግረዋልና ይህን ተካፍለው ጽፈዋል ። አንድም ነገር እንደ ሉቃስ ሄዳችሁ ንገሩልኝ ብሎ ሰዷቸዋል ኋላ ተከትሎ ሄዶ ተናግሯል ባሬ አማላጅ የላከ ሰው ተከትሎ ሄዶ ነገሩን እንዲናገር ይህን ተካፍለው ጽፈዋል ።

፮ ወሖረ እግዚእ ኢየሱስ ምስሌሆሙ ። ማቴ ፰፡፭ ።

፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከነሱ ጋራ ሄዶ።
ወአልጺቆ ኀበ ቤቱ ለውእቱ መስፍን ለአከ አዕርኪቲሁ ውእቱ መስፍን ኀቤሁ እንዘ ይብል እግዚኦ ኢትጻሙ ።
ወደቤቱ ሊገባ በቀረበ ጊዜ አቤቱ አትድከም ብሎ ወዳጆቹን ወደ ጌታ ላከ ።
እስመ ኢይደልወኒ ከመ ትባዕ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ።
ከቤቴ ጠፈር በታች ትገባ ዘንድ አይገባኝምና ።

፯ ወለልየ ኢይደልወኒ እምጻእ ኀቤከ ።
፯ እኔም ወዳንተ ልመጣ የማይገባኝ ነኝ ።
ወባሕቱ አዝዝ በቃልከ ።
ነገር ግን በቃልህ እዘዝ ።
ወየሐዩ ቍልዔየ ።
ብላቴናየም ይድናልና አለው ።

፰ እስመ አነሂ ብእሲ መኰንን አነ ።
፰ እኔም እንጂ ገዢ ነኝ ።
ወብየ ወዓልት ።
ተገዢዎች አሉኝ ።
ወዕብሎ ለዝ ሑር ወየሐውር ።
ይህን ሂድ እለዋለሁ ይሄዳል ።
ወለካልኡኒ ነዓ ወይመጽእ ።
ሌላውንም ና ፡ እለዋለሁ ይመጣል ።
ወለገብርየኒ ግበር ከመዝ ወይገብር ።
ባሪያዬንም እንዲህ አድርግ እለዋለሁ ያደርጋል አለው ።

፱ ወሰሚዖ እግዚእ ኢየሱስ ዘንተ እምኔሁ አንከረ ።

፱ ጌታም ይህን በሰማ ጊዜ አደነቀ ።
ወተመይጠ ይቤሎሙ ለሕዝብ እለ ተለውዎ አማን እብለክሙ ኢረከብኩ ዘከመዝ ሃይማኖተ በውስተ እስራኤል ።
ወደሚከተሉትም ተመልሶ በእስራኤል ዘንድ እንዲህ ያለ እምነት አላገኘሁም ብየ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ።

፲ ወአተዉ እለ ተፈነዉ ረከብዎ ለቍልዔ በዘሐይወ ።

፲ የተላኩት ስትመለሱ ጊዜ ልጁን ድና አገኙት

፲፩ ወበሳኒታ ሖረ ሀገረ እንተ ስማ ናይን ።

፲፩ በነጋው ናይን ወደምትባል አገር ሄደ ።
ወሖሩ ምስሌሁ አርዳኢሁ ።
ደቀ መዛሙርቱ ተከትለውት ሄዱ ።
ወሕዝብኒ ብዙኅ ።
ብዙ ሰዎች ተከትለውት ሄዱ ።

፲፪ ወበጺሖ ኀበ አንቀጸ ሀገር ናሁ ረከበ ቀበረ ዕውረ ዘወልደ ብእሲት መበለት ።

፲፪ ከከተማው በር ሊገባ በቀረበ ጊዜ ያንዲት ድሃ ልጅ በቃሬዛ ተሸክመውት ሰዎች አገኘ ቀበረ ዕውረ ምውተ ዕውረ ይላል አስከሬን ቃሬዛ የተሸከሙ ሰዎች አገኘ ።
ወውእቱ ዋሕድ ለእሙ ።
እሱም ለናቱ አንድ ልጅ ነበር ።
ወብዙኃን ሰብአ ሀገር ሀለዉ ምስሌሃ ።
ብዙ ሰዎችም ከሷ ጋራ ነበሩ ።

፲፫ ወሶበ ርእያ እግዚእነ መሐራ ወትሣሃላ ላዕሌሃ ።

፲፫ ጌታም ባያት ጊዜ አዘነላት ይቅር አላትም።
ወይቤላ ኢትብክዪ ።
አታልቅሽ አላት ።
ወቀርበ ወአኀዘ ንፍቆ ፡
ቀርቦ ቃሬዛውን ያልጋውን ሸንኮሩን ያዘ ንፍቅ ይላል ነፍስ የተለየችው አስከሬኑን ያዘ ።

፲፬ ወቆሙ እለ ይጸውርዎ ።

፲፬ የተሸከሙት አውርደውት ቆሙ ።
ወይቤሎ ለከ እብለከ ወሬዛ ተንሥእ ።
አንተ ጐበዝ ተነሥ እልሃለሁ አለው ።

፲፭ ወተንሥአ ወነበረ ውእቱ በድን ።

፲፭ ያም በድን ተነሥቶ ተቀመጠ ።
ወተናገረ ርቱዓ ።
አቃንቶ ተናገረ ።
ወአወፈዮ ለእሙ ።
እሱን ለሷ ሰጠው ይርዳሽ ያጥባሽ ብሎ ወአወፈያ ይላል እሱን ሰጣት ርዳት አጥባት ብሎ ።

፲፮ ወፈርሁ ኵሎሙ ። ሉቃ.፭፳፮፡፲-፱ ዮሐ.፬፡፲፱
፲፮ ሁሉም ፍርሃት ያዛቸው ።
ወሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርን አመሰገኑት
ወይቤሉ ዓቢይ ነቢይ ተንሥአ ለነ ።
ታላቅ ነቢይ ተነሣልን አሉ ።
ወተሣሃሎሙ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ።
እግዚአብሔር ወገኖቹን ይቅር ብሏልና።

በእንተ ኢየሱስ ወበእንተ አርድዕተ ዮሐንስ መጥምቅ

፲፯ ወተሰምዓ ዝንቱ ነገር በኵሉ በሐውርተ ይሁዳ ።

፲፯ ይህ ነገር በይሁዳ አገር ሁሉ ተሰማ ።
ወበኵሉ በሐውርቲሃ ።
ባውራጃዋም ሁሉ ።

፲፰ ወነገርዎ አርድእቲሁ ለዮሐንስ ዘንተ ኵሎ ነገረ ።

፲፰ ይህንም ሁሉ ነገር ደቀ መዛሙርቱ ለዮሐንስ ነገሩት ።

፲፱ ወጸውዓ ዮሐንስ ፪ተ እምአርዳኢሁ ። ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፪

፲፱ ዮሐንስም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ጠርቶ ።
ወለአኮሙ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ።
ወደጌታ ላካቸው ።
እንዘ ይብል አንተኑአ ዘይመጽእ ።
ይመጣል የምንለው አንተ ነህን ።
ወሚመ ቦኑ ካልዕ ዘንሴፎ ።
ወይም ተስፋ የምናደርገው ሌላ አለን ብሎ ።

፳ ወበጺሖሙ እለ ለአኮሙ ኀቤሁ ይቤልዎ ዮሐንስ መጥምቅ ለአከነ ወይቤ አንተኑአ ዘይመጽእ ወቦኑ ካልዕ ዘንሴፎ ።

፳ ወደሱ የተላኩትም ሰዎች በደረሱ ጊዜ ይመጣል የምንለው አንተ ነህ ወይም ሌላ ነው ብሎ ዮሐንስ ወዳንተ ልኮናል አሉት ።

፳፩ ወፈወሶሙ ለብዙኃን ሶቤሃ እምአደዊሆሙ ወእምሕማሞሙ ።

፳፩ በዚያን ጊዜም ብዙ ሰዎችን ከጭንቅ ደዌያቸው ፈወሳቸው ወእምእጋንንት እኩያን ።
ከክፉ አጋንንትም ፤
ወለብዙኃን ዕውራን ጸገዎሙ ይርአዩ ።
ለብዙ ዕውራንም ያዩ ዘንድ ብርሃንን ሰጣቸው

፳፪ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ፡ኢሳ ፴፭፡፭-፮
ጌታም መለሰ ፤
ወይቤሎሙ ሑሩ ንግርዎ ለዮሐንስ ዘሰማዕክሙ ወዘርኢክሙ ፤

፳፪ ሂዱችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት ።
ዕውራን ይሬእዩ ።
ዕውራን ያያሉ ።
ወስቡራን የሐውሩ ።
አንካሶችም ይሄዳሉ ።
ወእለ ለምጽ ይነጽሑ ።
ለምጻሞችም ይነጻሉ ፤
ወጽሙማንኒ ይሰምዑ ።
የደነቆሩም ይሰማሉ ።
ወምዉታንኒ ይትነሥኡ ።
የሞቱትም ይነሣሉ ።
ወነዳያንኒ ይዜነዉ ወይትፌሥሑ ።
የተቸገሩትም ይከብራሉ ደስ ይላቸዋል ።

፳፫ ወብፁዕሰ ዘኢይትዓቀፍ ብየ ።
፳፫ በኔም የማይጠራጠር የተመሰገነ ነው ።

ዘከመ ወደሶ ኢየሱስ ለዮሐንስ መጥምቅ ።

፳፬ ወኀሊፎሙ አርዳኢሁ ለዮሐንስ አኀዘ ይበሎሙ ለሕዝብ በእንተ ዮሐንስ መጥምቅ ።

፳፬ የዮሐንስ መልክተኞች በሄዱ ጊዜ የዮሐንስ መጥምቅን ነገር ለሕዝቡ ይነግራቸው ጀመረ ።
ምንተኑመ ወፃእክሙ ገዳመ ትርአዩ ።
በምድረ በዳ ምን ልታዩ ወጥታችኋል ።
ብርዓት ህየድ ሐመልሚል እምነፋስ ።
ነፋሱ የሚያንቀሳቅሰው ሸንበቆን ነው ፤
፳፭ ወምንተኑመ ወፃእክሙ ትርአዩ ።
፳፭ ነገር ግን ምን ልታዩ ወጥታችኋል ።
ብእሴኑ ዘርሱይ በቀጠንተ አልባስ ።
ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን ልታዩ ወጥታችኋል ።
ናሁ እለሰ ርሱያን በአልባሰ ክብር ውስተ አብያተ ነገሥት ሀለዉ ።
የክብር ልብስ የለበሱ ግን እንደሆኑ ከነገሥታት ቤት አሉ።

፳፮ ወምንተኑመ ወፃእክሙ ትርአዩ ።
፳፮ ወይስ ምን ልታዩ ወጥታችኋል ነቢየኑ ነቢይን ነው ።
አወ እብለክሙ የዓቢ እምነቢይ ።
አዎን ከነቢይ ይበልጣል ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፳፯ ዝንቱ ውእቱ ዘበእንቲአሁ ተጽሕፈ ናሁ አነ እፌኑ መልአኪየ ቅድመ ገጽከ ዘይጼይሕ ፍኖተከ ቅድሜከ ። ሚል ፫ ፡ ፩ ማቴ ፲፩ ፡ ፲ ማር ፩ ፡ ፪ ።

፳፯ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተነገረለት ይህ ነው ።

፳፰ አማን እብለክሙ ኢይትነሣእ እምትውልደ አንስት ዘየዓቢ እምዮሐንስ መጥምቅ ወኢመኑሂ ።

፳፰ ከሴቶች ከሚወለዱ ወገን ከዮሐንስ የሚበልጥ ማንም ማን እንደሌለ በውነት እነግራችኋለሁ ።
፳፱ ወበመንግሥተ ሰማያትሰ ዘይንእስ የዓብዮ።
፳፱ በመንግሥተ ሰማያት ግን ታናሹ ከሱ ይበልጣል ።

ወሰሚዖሙ ኵሎሙ ሕዝብ ወመጸብሐን አጽደቅዎ ለእግዚአብሔር ።
ሕዝቡ ሁሉ ቀራጮችም ነገሩን ሰምተው እውነት ነው አሉ ።
እስመ ተጠምቁ ጥምቀተ ዮሐንስ ።
በዮሐንስ ጥምቀት ተጠምቀው ነበረና ።

፴ ወፈሪሳውያንሰ ወጸሐፍተ ሕግ ዓለዉ ትእዛዘ እግዚአብሔር ።

፴ ፈሪሳውያንና የሕግ ጸሐፊዎች ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፈረሱ ።
እስመ ኢተጠምቁ በኀቤሁ ።
በሱ ዘንድ አልተጠመቁምና ።

፴፩ በምንት አስተማስሎሙ ለሰብእ ዛቲ ትውልድ ። ማቴ. ፲፩ ፡ ፲፮ ።

፴፩ የዚችን ትውልድ ሰዎች በምን እመስላቸዋለሁ ።
ወመኑ ይመስሉ ።
ማንን ይመስላሉ ።

፴፪ ይመስሉ ደቂቀ እለ ይነብሩ ውስተ ምስያጥ ።

፴፪ በገበያው ተቀምጠው ።
ወይጼውዑ ቢጾሙ ።
ባልንጀሮቻቸውን ጠርተው ፤
ወይቤልዎሙ ኃለይነ ለክሙ ወኢዘፈንክሙ ።
የዘፈን ዜማ ቀነቀንላችሁ አልዘፈናችሁም ።
አስቆቀውነ ለክሙ ወኢበከይክሙ ።
አለቀስንላችሁ አላለቀሳችሁም የሚሉ ብላቴኖችን ይመስላሉ ።

፴፫ እስመ መጽአ ዮሐንስ መጥምቅ ኢይበልዕ እክለ ወኢይሰቲ ወይነ ። ማቴ ፫ ፡ ፬ ማር ፡ ፩ ፡ ፮

፴፫ ዮሐንስ መጥምቅ እህል ሳይበላ ጠጅ ሳይ ጠጣ መጥቷልና ።
ወትቤልዎ ጋኔን ቦቱ ።
ጋኔን አድሮበታል አላችሁት ።

፴፬ ወመጽአ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ይበልዕ ወይሰቲ ።

፴፬ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ግን እየበላ እየጠጣ መጣ ።
ወትቤሉ ነዋ ብእሲ በላዒ ወሰታዬ ወይን ።
እነሆ የሚበላ ጠጅም የሚጠጣ ሰው ።
እርከ መጸብሐን ወኃጥአን ።
የቀራጮችና የኃጥአን ወዳጅ አላችሁት ።

፴፭ ወጸድቀት ጥበብ እምኵሉ ውሉዳ ።

፴፭ ጥበብ ወልድ ከልጆችዋ ሁሉ ይልቅ ከበረች

በእንተ ፈሪሳዊ ወኃጥዕት ብእሲት ፤

ወእንዘ ሀለው እግዚእ ኢየሱስ ዝየ ይቤሎ አሐዱ እምፈሪሳውያን ከመ ይምሳሕ በኀቤሁ ።
በሱ ዘንድ ምሳ ይበላ ዘንድ ከፈሪሳውያን አንዱ ለመነው ።

፴፮ ወቦአ ቤተ ፈሪሳዊ ወረፈቀ ።

፴፮ ከፈሪሳዊ ቤት ገብቶም ተቀመጠ ።

፴፯ ወመጽአት ብእሲት ኃጥዕት እምሰብአ ይእቲ ሀገር እእሚራ ከመ ይመስሕ ውስተ ቤተ ፈሪሳዊ ወተማየጠት ዕፍረተ ዘእልባበጥሮስ ። ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፯ ማር ፡ ፲፬ ፡ ፫ ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ።

፴፯ በዚያ አገር ካሉ ሰዎች ኃጢአተኛ ሴት ከፈሪሳዊ ቤት እንዲበላ ባወቀች ጊዜ የደቀቀ የጣፈጠ ሽቱ ገዝታ መጣች ።

፴፰ ወቆመት ድኅሬሁ ኀበ እገሪሁ ።

፴፰ ከወደኋላው በእግሩ አጠገብ ቆመች ። ሐተታ ጌታ እንደ ግብጻውያን አቀማመጥ እግሩን ወደኋላው አድርጎ ተቀመጦ ነበርና ። አንድም ወንበሩ እንደ አፍርንጆች ወንበር እግር ወደኋላ የሚያደርግ ነው ። አንድም ወደ እግሩ ለማለፍ በኋላው ቆመች ።
ወበከየት ወአርሐሰት እገሪሁ በአንብዓ ።
እያለቀሰች እግሩን በዕንባዋ አጠበችው ።
ወትመዘምዝ በሰእርተ ርእሳ ።
በራሷ ጠጕርም አበሰችው ።
ወትስእም እገሪሁ ፤
እግሩንም ትስመው ነበር ።
ወትቀብዖ ዕፍረተ ፤
ሽቱም ትቀባው ነበር ።

፴፱ ወርእዮ ፈሪሳዊ ዘጸውዖ ሐለየ በልቡ ።

፴፱ የጠራው ፈሪሳዊ አይቶ በልቡ አሰበ ።
ወይቤ ሶበሁ ነቢይ ውእቱ ዝንቱ ።
ይህ ነቢይማ ቢሆን ።
እምኢያእመረ ከመ ኃጥእት ዛቲ ብእሲት እንተ ትገሥሦ ።
ይፀች የምትዳስሰው ኃጥእት እንደሆነች ባላወቀም ነበር ብሎ ተናገረ ።

፵ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።

፵ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መለሰ ።
ወይቤሎ ስምዖን ስምዖንብየ ዘእብለከ ።
ስምዖን ሆይ የማስፈረድህ ነገር አለኝ አለው ።
ወይቤሎ እ ሊቅ በል ።
መምህር ሆይ ተናገር አለው ።

፵፩ ወይቤሎ ክልኤቱ ይፈድዩዎ ለአሐዱ በዓለ እዳ ።

፵፩ ላንድ ሰው ሁለት ባለዳች አሉት ።
አሐዱ ይፈድዮ ኃምስተ ምእተ ዲናረ ።
አንዱ አምስት መቶ ወቄት ይከፍላል ።

ወካልዑኒ ሃምሳ ።
ሁለተኛውም አምሳ ወቄት ይከፍለዋል ።

፵፪ ወኃጢአሙ ዘይፈድዩ ኅደገ ሎሙ ለክልኤሆሙ ።

፵፪ የሚከፍሉት ባያገኙ ለሁለቱም ተወላቸው ።
፵፫ መኑ እንከ ርቱዕ ፈድፋደ ያፈቅሮ እምኔሆሙ ።

፵፫ ከነሱ ማናቸው አብልጦ ሊወደው ይገባዋል አለው ።
ወተሠጥወ ስምዖን ።
ስምዖንም መለሰ ።
ወይቤ እብለከ ዘብዙኃ ኃደገ ሎቱ ።
ፍረድስ ካልኸኝ አምስት መቶ ወቄት የተወለት አብልጦ ሊወደው ይገባዋል አለው ።
ወይቤሎ ስምዖን ሠናየ ፈታሕከ ።
ስምዖን ሆይ መልካም ፈረድህ ።
እሙነ ፈታሕከ ።
እውነት ፈረድህ አለው ።

፵፬ ወተመይጠ ኀበ ይእቲ ብእሲት ።
፵፬ ወደዚያች ሴት ተመለሰ ።
ወይቤሎ ለስምዖን ትሬኢያኑ ለዛቲ ብእሲት ።
ስምዖንን ይህችን ሴት ታያታለህን አለው ።
ቦእኩ ቤተከ ።
አቤትህ ገባሁ ።
ወኢወሀብከኒ ማየ ጥቀ ለእገርየ ።
ለእግሬ ውኃ እንኳን አልሰጠኸኝም ።
ወይእቲሰ በከየት ወበአንብዓ አርሐሰተኒ እገርየ ።
ይህች ግን ለቀሰች በእንባዋ እግሬን አጠበች ።
ሐተታ ትእምርተ ንስሐ ነው ።
ወበሰዕርተ ርእሳ መዝመዘተኒ በራሷ ጸጉርዋ አደፈችኝ ። ሐተታ ትእምርተ ትሕትና ነው ።

፵፭ ወአንተሰ ኢሰዓምከኒ ።
፵፭ አንተስ እጅ አልነሣኸኝም ።
ወይእቲሰ እምጊዜ ቦእኩ ኢያቋረጸት ስዒመ እገርየ ።
እሷ ግን ከገባሁ ጀምሮ እምጊዜ ቦአት ከገባች ጀምሮ እግሬን ተመሳም አላቋረጠችም ሐተታ ፤ ትእምርተ ፍቅር ነው ።

፵፮ ወአንተሰ ኢቀባእከኒ በዘይት ርእስየ ።
፵፮ ዘይት ሲሉ ነው ። አንተስ ዘይት ቅብኣ አልቀባኸኝም ።
ወይእቲሰ ዕፍረተ ቀብዓተኒ እገርየ ።
እሷ ግን እግሬን ሽቱ ቀባችኝ ። ሐተታ ትእምርተ አክብሮ ሽቱ ከዘይት እንዲበልጥ በዚህ ይታወቃል ።

፵፯ ወበእንተዝ እብለከ ተኀደገ ኃጢአታ ብዙኅ
፵፯ ስለዚህ ነገር ብዙ ኃጢአቷ ቀረላት ብዬ እነግርሃለሁ ።
እስመ ብዙኃ አፍቀረተኒ ።
ብዙ ወደደችኝና ።
ወዘሰ ውኁደ አፍቀረኒ ውኁድ ኃጢአት ይትኃደግ ሎቱ ።
ጥቂት የሚወደኝ ጥቂት ኃጢአት ይወርድለታል ።

፵፰ ወይቤላ ለይእቲ ብእሲት ተኀድገ ለኪ ኃጢአትኪ ። ማቴ፡፱ ፡ ፪ ።

፵፰ አሷንም ኃጢአትሽ ቀርቶልሻል አላት ። ሐተታ እሷን ብዙን አፍቀረተኒ አለ ። ሽቱ የተገዛበት አምስት መቶ ወቄት ነውና ። እሱን ውኁደ አፍቀረኒ አለ ምሳው የተገዛ ባምሳ ወቄት ነውና ። እሷን ብዙን ኃጢአታ አላት ዘማ ናትና ። እሱን ውኁደ ኃጢአቱ አለ ጽሕፍት ፈሪሳውያን ምንም ውዳሴ ከንቱ ቢያስቀርባቸው ዓሥሩን ቃላት አንጠብቃለን ባዮች ናቸውና ።

፵፱ ወአኀዙ እለ ይረፍቁ ይበሉ በበይናቲሆሙ መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘየኀድግ ኃጢአተ ።

፵፱ ለመብል የተቀመጡት ይህ ኃጢአትን ይቅር የሚል ማነው አሉ ።
ወካዕበ ይቤላ ለይእቲ ብእሲት ሃይማኖትኪ አሕየወተኪ እትዊ በሰላም ።
ሃይማኖትሽ አድኖሻልና በፍቅር ሂጂ አላት ።

ዘከመ ዖደ ኢየሱስ አህጉረ ገሊላ ።

ምዕራፍ ፰ ።

፩ ወእምዝ በሳኒታ አንሶሰወ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ አህጉር ወአእፃዳት ።

፩ ከዚህ በኋላ በነጋው በየሀገሩና በመንደሩ ተመላለሰ ።
ወሰበከ ሎሙ ።
ሰበከላቸው ።
ወመሐሮሙ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
ስለ እግዚአብሔር መንግሥትም አስተማራቸው ።
ወምስሌሁ ዓሠርቱ ወክልኤቱ አርዳኢሁ ።
ዐሥራሁለቱም ከሱ ጋራ ነበሩ ።

፪ ወአንስትኒ እለ አሕየዎን እምአጋንንት እኩያን ወእምደዌሆን ። ማር ፲፮ ፡ ፱ ።

፪ ከክፉ አጋንንትና ከደዌያቸው የፈወሳቸውም ሴቶች ።
ወእማንቱ ማርያም እንተ ይብልዋ መግደላዊት እንተ ሰብዐቱ አጋንንት ወፅኡ እምኔሃ ።
ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የሚሏት ማርያም ።

፫ ወዮሐና ብእሲተ ኩዛ መጋቢሁ ለሄሮድስ ።
፫ የሄሮድስ ምግብ ቤቱ የኩዛ ሚስት ዮሐና ።

ወሶስና ወካልዓትሂ ብዙኃት እለ ተልእክዎ በንዋዮን ። በገንዘባቸው ያገለገሉት ማለት በሕዋሳቶቻቸው ንጽሕናን ይዘው ያገለገሉት ሌሎችም ብዙ ሴቶችና ሶስናም ነበሩ ። ዘበእንተ ንዋይየ ተቀደሰት ሊተ ነፍስየ እንዲል ።

በእንተ ምሳሌ ዘዘራኢ ።

፬ ወእንዘ ያጸምዕዎ ኵሎሙ ሕዝብ ።
፬ ሕዝቡም ሁሉ ሲሰሙት ።
ወእለሂ መጽኡ ኀቤሁ እምኵሉ አህጉር ።
ከየሀገሩም የመጡ አሉ ።
ይቤሎሙ ምሳሌ እንተ ከመዝ ።
እንዲህ ያለ ምሳሌ ነገራቸው ።

፭ ወፈረ ዘይዘርዕ ከመ ይዝራዕ ።
ዘርዖ ። ማቴ ፲፫ ፡ ፫ ማር ፬ ፡ ፫

፭ የሚዘራ ገበሬ ዘሩን ሊዘራ ወጣ ።
ወእንዘ ይዘርዕ ቦ ዘወድቀ ውስተ ፍኖት ።
ሲዘራም ከመንገድ የወደቀ ዘር አለ ።
ወመጽአ ወኬድዎ ሰብእ ወበልዕዎ አዕዋፈ ሰማይ ።
ሰዎች መጥተው የረገጡት የሰማይ ወፎችም የበሉት ።

፮ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ኰኵሕ ።
፮ ከጭንጫም የወደቀ ዘር አለ ።
ወበቊሎ የብሰ በጊዜሃ ።
በበቀለ ጊዜም ፈጥኖ የደረቀ ።
እስመ አልቦ ሥርው ።
ሥር የለውምና ።

፯ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ሦክ ።
፯ ከሾህ ውስጥ የወደቀ አለ ።
ወበቊሎ ጠበቆ ሦክ ።
በበቀለም ጊዜ እሾህ አንቆ የያዘው ።

፰ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ሠናይት ።
፰ በመልካም ምድር የወደቀም አለ ።
ወሶበ በቊለሂ ፈረየ ምእተ ምክዕቢተ ።
በበቀለም ጊዜ መቶ ዕጽፍ አፈራ ።
ወዘንተ ብሂሎ ይቤሎሙ ዘቦ ዕዝን ሰሚዓ ለይስማዕ ።
ይህን ተናግሮ ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ አላቸው ።

፱ ወተስእልዎ አርዳኢሁ ።
፱ ደቀ መዛሙርቱ ጠየቁት ።
ወይቤልዎ ምንትኑ ይእቲ ዛቲ ምሳሌ ።
ይህች ምሳሌ ምንድናት አሉት ።

፲ ወይቤሎሙ ለክሙ ተውህበ ታእምሩ ምሥጢራ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ። ኢሳ ፮ ፡ ፱ ማቴ ፲፫ ፡ ፲፬ ማር ፬ ፡ ፲፪ ዮሐ ፲፪ ፡ ፵ ግብ ፳፰ ፡ ፳፮ ሮሜ ፲፩ ፡ ፰

፲ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ለናንተ ተሰጥቷል ።
ወለእለካቲሰ በምሳሌ ።
ለቀሩት ግን በምሳሌ ።
ከመ ርእዮሙኒ ኢይርአዩ ።
አይተው እንዳያዩ ።
ወሰሚዖሙኒ ኢይሰምዑ ።
ሰምተው እንዳይሰሙ ።
ወኢይለብዉ ።
እንዳያስተውሉም ።

፲፩ ወከመዝ ምሳሌሁ ።
፲፩ ምሳሌውም ይህ ነው ።
ዘርዕሰ ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ ።
ዘሩም ቃለ እግዚአብሔር ነው ።

፲፪ ወዘሰ ውስተ ፍኖት ወድቀ እሉ እሙንቱ እለ ይሰምዑ ቃለ ።

፲፪ በመንገድ የወደቀውንም ዘር ነገር የሚሰሙ ፤
ወይመጽእ ሰይጣን ወይነሥእ ለቃል እምልቦሙ ከመ ኢይእመኑ ወኢይሕየዉ ።
አምነው እንዳይድኑ ሰይጣን መጥቶ ነገሩን ከልቡናቸው የሚወስድባቸው ናቸው ።

፲፫ ወዘሰ ውስተ ኰኵሕ ወድቀ ።
፲፫ በጭንጫ የተዘራውም ።
ወሰሚዖሙ ይትዌከፍዎ በፍሥሐ ።
በሰሙ ጊዜም ነገሩን ደስ ብሏቸው የሚቀበሉ ።
ወባሕቱ ሥርው አልቦሙ ሶቤሃ ዳእሙ የአምኑ ።
ነገር ግን ለጊዜው ያምናሉ እንጅ መሠረት የላቸውምና ።
ወእምከመ ተመንደቡ የዓልዉ ።
በመከራ በተጨነቁ ጊዜ ይክዳሉ ።

፲፬ ወዘሰ ውስተ ሦክ ወድቀ ።
፲፬ ከሾህ ውስጥ የወደቀውም ።
እሉ እሙንቱ እለ ይሰምዑ ቃለ ወሕሊና ብዕል ።
እኒህም ነገሩን ሰምተው የባለጠግነት አሳብ ።
ወትካዘ መንበርት ።
የመኖሪያ መቈርቈር ።
ወሐውዘ ተድላ ወፈገዕ ያጠውቆሙ ወኢይገብሩ ፍሬ ።
የተድላ የደስታም መጣፈጥ አስጨንቋቸው የማይሠሩት ናቸው ።

፲፭ ወዘሰ ውስተ ምድር ሠናይት ።
፲፭ ከመልካሙ የተዘራው ግን ፤
እሉ እሙንቱ እለ ይሰምዑ ቃለ በሠናይ ልብ ወያዐቅብዎ ወበ[illegible] ይትዓገሡ [illegible]
ነገሩን በበጎ ልቡና ሰምተው የሚታገሡ [illegible]
ወያጠብዎ ። [illegible] የሚጠብቁ [illegible]
ወይፈርዩ ። [illegible] የሚያፈሩ ናቸው ።

፲፮ ወአልቦ ዘያኀቱ ማኅቶተ ወይከድና ንዋየ
ወያነብራ ታሕተ ዓራት ። ማቴ ፭ ፡ ፲፭ ማር ፬ ፡ ፳፩ ።

፲፮ መብራት አብርቶ በዕቃ ከድኖ ከአልጋ በታች
የሚያኖር የለም ።
ዘእንበለ ዲበ ተቅዋማ ።
ከመቅረዟ ላይ ነው እንጂ ።
ከመ ፡ ይርአዩ ብርሃነ እለ ያንሶሰው ።
የሚመላለሱ ብርሃንን ያዩ ዘንድ ።

፲፯ ወአልቦ ኅቡእ ዘኢይትከሠት ። ማቴ ፡
፲ ፡ ፳፮ ማር ፡ ፬ ፡ ፳፪ ።

፲፯ የማይገለጥ የተሸሸገ የለም ።
ወአልቦ ክዱን ዘኢያስተርኢ ።
የማይታይ የተሰወረ የለም ።
ወገሃደ ይከውን ።
ይገለጣል እንጂ ።

፲፰ ወአእምሩ እንከ ይእዜ ዘከመ ትሰምዑ ።
ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ።

፲፰ እንግዲህ እንደምትሰሙት አስተውሉ ።
እስመ ለዘቦ ይሁብዎ ወይዌስክዎ ።
ላለው ይሰጡታል ይጨምሩለታል ።
ወለዘሰ አልቦ እስኪ ቦ የሃይድዎ ።
የሌለውን ግን ያለውን ይቀሙታል ።

በእንተ አኀዊሁ ለኢየሱስ ።

፲፱ ወመጽኡ ኀቤሁ እሙ ወአኀዊሁ ። ማቴ ፡
፲፪ ፡ ፵፮ ማር ፫ ፡ ፴፩ ።
፲፱ እናቱና ወንድሞቹ ወደሱ መጡ ።
ወስእኑ ረኪቦቶ እስመ ጽፉቅ ሰብእ ።
ሰው ስለበዛ እሱን ማግኘት ተሳናቸው ።
፳ ወይቤልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ እምከ ወአኀዊከ አፍአ ይቀውሙ ።
፳ እናትህና ወንድሞችህ ከውጭ ቆመዋል ።
ወይፈቅዱ ይርአዩከ ።
ሊያዩህ ይወዳሉ ብለው ነገሩት ።
ወአውሥአ ። እሱም መለሰ ።
፳፩ ወይቤሎሙ እምየ ወአኀውየ እለ ይሰምዑ ቃለ እግዚአብሔር ወይገብርዎ ።
፳፩ እናቴም ወንድሞቼም የእግዚአብሔርን ነገር ሰምተው የሚያደርጉት ናቸው ።

በእንተ ኀድአተ ባሕር ።

፳፪ ወኮነ በአሐቲ ዕለት ዐርጉ ውስተ ሐመር ውእቱ ወአርዳኢሁ ።
፳፪ ከዕለታት ባንድ ቀን እሱም ደቀ መዛሙርቱም ወደ መርከብ ወጡ ።
ወይቤሎሙ ንዑ ንዕዱ ማዕዶተ ቀላይ ።
ኑ ወደ ወንዝ ማዶ እንሂድ አላቸው ።
ወሖሩ ። ሔዱ ።

፳፫ ወእንዘ የሐውሩ ኖመ ።
፳፫ ሲሄዱ ጌታ ተኛ ።
ወመጽአ ነፋስ አውሎ ውስተ ባሕር ።
አውሎ ነፋስ መጣ ።
ወመልአ ማየ ሐመርሙ ።
መርከባቸውን ውኃ መላው ።
ወተመንደቡ ። ተጨነቁ ።

፳፬ ወሖሩ ኀቤሁ ወአንቅሕዎ ።
፳፬ ሄደውም ቀሰቀሱት ።
ወይቤልዎ ኦ ሊቅ አድኅነነ ከመ ኢንሙት ።
መምህር ሆይ እንዳንሞት አድነን አሉት ።
ወተንሥአ ወገሠጾሙ ለነፋሳትኒ ወለማዕበለ ባሕርኒ ።
ተነሥቶ ነፋሱንም ማዕበሉንም ገሰጻቸው ።
ወአርመሙ ። ዝም አሉ ።
ወኮነ ዛሕነ ዐቢየ ።
ታላቅ ጸጥታ ተደረገ ።

፳፭ ወይቤሎሙ አይቴ ሃይማኖትክሙ ።
፳፭ ሃይማኖታችሁ የታል አላቸው ።
ወፈርሁ ። ፈሩ ።
ወአንከሩ ። አደነቁም ።
ወይቤሉ በበይናቲሆሙ መኑ እንጋ ዘይትኤዘዙ ሎቱ ባሕርኒ ወነፋሳትኒ ።
ውኃና ነፋስ የሚታዘዙለት ይህ ማነው እንጃ አሉ ።

ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ በብሔረ ጌርጌሴኖን ለዘቦቱ ጋኔን ።

፳፮ ወእምዝ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ በሐመር ሀገረ ጌርጌሴኖን በአንጻረ ማዕዶተ ገሊላ ።

፳፮ በገሊላ ማዶ አንጻር ወዳለች ወደ ጌርጌሴኖን ሄደ ።

፳፯ ወወሪዶሙ ምድረ ተቀበሎ ብእሲ ዘጋኔን ወፂኦ እምሀገር ።

፳፯ ከመርከቡ በወረዱ ጊዜም ጋኔን ያደረበት ሰው ተቀበለው ።
ወጕንዱይ መዋዕል እምዘኢለብሰ ልብሰ ።
ከብዙ ዘመን ጀምሮ ልብስ አይለብስም ነበር ።
ወኢቦአ ቤተ ።
ከቤትም ገብቶ አያውቅም ነበር ።
ዳዕሙ ይነብር ውስተ መቃብር ።
በመቃብር ይኖር ነበር እንጂ ።

፳፰ ወሶበ ርእዮ ለእግዚእ ኢየሱስ ከልሐ ወሮጸ ወሰገደ ሎቱ ፤

፳፰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ባየው ጊዜም
[illegible]
ወአውየወ በዓቢይ ቃል ።
በታላቅ ቃል እሰምቶ ተናገረ ።
ወይቤ ምንት ብየ ምስሌከ ወልደ እግዚአብሔር
ልዑል [illegible]
የልዑል እግዚአብሔር ልጅ [illegible] ካንተ
ጋራ ምን ጸብ አለኝ ።
እስተበቍዐከ ኢትሣቅየኒ ።
እንዳያሠቃየው ማለደው ።

፳፱ እስመ [illegible] ለውእቱ ርኩስ ጋኔን [illegible]
እምላዕሌሁ ውእቱ ብእሲ [illegible]

፳፱ [illegible] ጋኔን ከሰውየው ላይ [illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] ነበርና ።
ወይሞቅሕዎ በመዋቅሕት ።
በሰንሰለት ያስሩት ነበር ።
ወየዓቅብዎ ደቂቅ ።
ሕፃናት ይጠብቁት ነበር ።
ወይሰብር መዋቅሕቲሁ ።
ሰንሰለቱን ይሰብር እግር ብረቱንም [illegible]
[illegible]
[illegible] ነበር ።

፴ ወተስእሎ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ምንት
ስምከ ።

፴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስምህ ማነው ብሎ
ጠየቀው ።
ወይቤሎ ሌጌዎን ስምየ ።
ስሜ ሌጌዎን ነው አለው ።
እስመ ብዙኃን አጋንንት [illegible] ።
ብዙ አጋንንት አድረውበት ነበርና ።

፴፩ ወአስተብቍዕዎ ከመ ኢይፈንዎሙ ውስተ
ማዕምቅት ይረዱ ውስተ ሲኦል ።

፴፩ ወደ ሲኦል ይወርዱ ዘንድ እንዳያዛቸው
ለመኑት ።

፴፪ ወበህየ መራዕየ አሕርው ብዙኅ ይትረዐይ
ውስተ ደብር ።

፴፪ ከተራራው ላይ ተሰማርተው ብዙ የእሪያ መንጋ
ከዚያ ነበር ።
ወአስተብቍዕዎ እሙንቱ አጋንንት ከመ ያብሖሙ
ይባኡ ላዕለ አሕርው ።
ያድሩባቸው ዘንድ እንዲያሰናብታቸው ማለዱት ።
ወአብሖሙ ።
አሰናበታቸው ።

፴፫ ወወፂአሙ እሙንቱ አጋንንት [illegible]
ውእቱ ብእሲ [illegible]

፴፫ አጋንንቱ ከዚያ ሰው [illegible]
በእሪያዎች አደሩባቸው ።
ወዓብዱ ኵሉ መራዕየ አሕርው ወወድቁ እንተ
ጽድፍ ወውሕዙ ቀላየ ወሞቱ ።
እሪያም የሪያ መንጋ ወደገደል ወድቀው ወደባሕር
ገብተው ሞቱ ።

፴፬ ወርእዩ [illegible]

፴፬ ጠባቂዎች አይተው [illegible]
ወአተዉ ወዜነዉ [illegible]
ሄደውም በየሀገሩ በየመንደሩ [illegible]

፴፭ [illegible]
[illegible] ወፅኡ [illegible]
ሄዱ ።
ወበጽሑ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታም ካለበት ደረሱ ።
ወረከብዎ ለውእቱ ብእሲ ዘወፅኡ እምኔሁ አጋንንት
እንዘ ይነብር ኀበ እገሪሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ያን አጋንንት የወጡለትን ሰው ከጌታችን ከኢየሱስ
ክርስቶስ እግር አጠገብ ተቀምጦ አገኙት ።
ወልቡስ ልብሶ ።
ልብሱን ለብሶ ።
ወንቢአ ልቡ ።
አእምሮው ተመልሶለት ።
ወፈርሁ ።

፴፮ ወነገርዎሙ እለ ርእዩ ዘከመ ሐይወ
ዘቦቱ ጋኔን ።

፴፮ ያዩት ሰዎችም ያ ጋኔን ያደረበት ሰው
እንደ ዳነ ነገሯቸው ።

፴፯ ወአስተብቍዕዎ [illegible]
[illegible] ከመ ይሑር እምኀቤሆሙ ።

፴፯ የጌርጌሴኖን አውራጃ ሰዎች ሁሉ ይሄድ
ዘንድ ማለዱት ።
እስመ [illegible] ።
ጽኑ ፍርሃት ይዟቸዋልና ።
ወዓርገ ሐመረ እግዚእ ኢየሱስ ወተመይጠ ።
ጌታም በመርከብ ተጭኖ ተመለሰ ።

፴፰ ወአስተብቍዖ ለእግዚእ ኢየሱስ ውእቱ
ብእሲ ዘወፅኡ እምኔሁ አጋንንት ከመ ይሑር ምስሌሁ ።

፴፰ ያም አጋንንት የወጡለት ሰው ከሱ ጋራ
ይሄድ ዘንድ ጌታን ማለደው ።

፴፱ ወፈነዎ ወይቤሎ ሑር [illegible]
ግብር ኵሎ ዘገብረ ለከ እግዚአብሔር ።

፴፱ ወደቤትህ ተመልሰህ እግዚአብሔር የሠራልህን ሥራ ሁሉ ንገር ብሎ አሰናበተው ።
ወሖረ ውስተ ኵሉ አህጉር ወነገረ ኵሎ ዘገብረ ሎቱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ።
ያደረገለትን ሁሉ ተናገረ ።

፵ ወሶበ ተመይጠ እግዚእ ኢየሱስ ተቀበልዎ ሕዝብ ኀቡረ ።

፵ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተመለሰ ጊዜም ሕዝቡ ሁሉ ተቀበሉት ።
እስመ ኮኑ ኵሎሙ ይጸንሕዎ ።
ሁሉም ይጠብቁት ነበርና ።
በእንተ ወለተ ኢያኢሮስ ወበእንተ ደም ዘይውኅዛ ።

፵፩ ወመጽአ ብእሲ ዘስሙ ኢያኢሮስ ፤ ማቴ ፱ ፲፰ ማር፡፭ ፳፪ ።

፵፩ ኢያኢሮስ የሚባል ሰው መጣ ፤
ወውእቱ መጋቤ ምኵራብ ።
እሱም የጉባኤ አለቃ ነበር ።
ወሰገደ ሎቱ ታሕተ እገሪሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ከጌታ እግር በታች ሰገደ ።

፵፪ ወአስተብቍዖ ይባእ ቤቶ ።
፵፪ ከቤቱም ይገባ ዘንድ ማለደው ።
እስመ ቦቱ እሐቲ ወለት ።
አንዲት ልጅ ነበረችውና ።
ዘ፲ቱ ወ፪ቱ ክረምታ ።
ዐሥራ ሁለት ዘመን ሁንዋት ነበር ።
ወይእቲ አልጸቀት ትሙት ።
እሷም ልትሞት ቀርባ ነበር ።
ወእምዝ እንዘ የሐውር ምስሌሁ እግዚእ ኢየሱስ ይትጋፍዕዎ ሰብእ ።
ከዚያ በኋላ ጌታ ከሱ ጋራ ሲሄድ ሰዎች ይገፉት ነበር

፵፫ ወመጽአት ብእሲት እንተ ደም ይውኅዛ እም፲ቱ ወ፪ቱ ክረምት ።

፵፫ ካሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴትም መጣች ወአሕለቀት ንዋያ ለዓቀብተ ሥራይ ገንዘቧንም ሁሉ ለባለመድኃኒት ሰጥታ ጨርሳ ነበር
ወአልቦ ዘክህለ ፈውሶታ ።
ሊያድናት የተቻለው የለም ።

፵፬ ወቀርበት ወቆመት እንተ ድኅሬሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፵፬ ቀርባ በጌታችን በኢየሱስ ኋላ ቆመች ፤
ወገሠሠት ጽንፈ ልብሱ ።
የልብሱን ጫፍም ዳሰሰች ።
ወቆመ ሶቤሃ ውኅዘተ ደማ ።
የደሟ ጉርፍ ያንጊዜውን ቆመ ።

፵፭ ወይቤ እግዚእ ኢየሱስ መኑ ገሠሠኒ ።
፵፭ ጌታችን ኢየሱስክርስቶስም የዳሰሰኝ ማነው አለ ።
ወክሕዱ ኵሎሙ ።
ሁሉም ካዱ ።

፵፮ ወይቤልዎ ጴጥሮስ ወእለሂ ምስሌሁ ። ሊቅ እኮኑ ሰብእ ይጣወቅ ወይጸዓቅ ።

፵፮ ጴጥሮስና ከሱ ጋራ የነበሩ መምህር ሆይ ሰው ይጋፋ ይጨናነቅ የለምን ።
ወትብል ፡ መኑ ገሠሠ ልብስየ ።
ልብሴን ማን ዳሰሰው ትለናለህ አሉት ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ቦ ዘገሠሠኒ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የዳሰሰኝ አለ ።
እስመ አነ አእምር ከመ ኃይል ወፅአ እምኔየ ።
ኃይል ከኔ እንደወጣ አውቃለሁና አላቸው ።

፵፯ ወርእያ ይእቲ ብእሲት ከመ ኢተክብተ ላቲ ርዕደት ።

፵፯ ያችም ሴት እንዳልተሸሸገላት ባየች ጊዜ ተንቀጠቀጠች ።
ወሖረት ወሰገደት ሎቱ ።
ሄዳ ሰገደችለት ።
ወነገረት በቅድመ ኵሉ ሕዝብ በእንተ እይ ግብር ዘቀርበት ኀቤሁ ወገሠሠት ጽንፈ ልብሱ ዘከመ ሐይወት ሶቤሃ ።
ስለማናቸውም ሥራ ቀርባ የልብሱን ጫፍ ዳሰሳ ያን ጊዜውንም ፈጥና እንደዳነች በሕዝቡ ሁሉ ፊት ተናገረች ።

፵፰ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ እመኒ ወለትየ ሃይማኖትኪ አሕየወተኪ ።

፵፰ ልጄ ሆይ ሃይማኖትሽ አድኖሻልና
እመኚ አላት ።
እትዊ በሰላም ። በደህና ሂጂ አላት ።

፵፱ ወእንዘ ዘንተ ይትናገር መጽአ አሐዱ እምቤተ መጋቤ ምኵራብ ወይቤሎ ወለትከሰ ሞተት።

፵፱ ይኸን ሲናገር ከጉባኤው ሹም ቤት አንድ ሰው መጥቶ ልጅህ ሞታለች አለው ።
ወኢታጻምዎ እንከ ለሊቅ ።
እንግዲህ መምህርን አታድከመው ።

፶ ወሰሚዖ እግዚእ ኢየሱስ ይቤሎ ለመጋቤ ምኵራብ ኢትፍራህ ዳዕሙ ተአመን ።

፶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን በሰማ ጊዜ እመን እንጂ አትፍራ አለው ።
ወለትከሰ ተሐዩ ።
ልጅህም ትድናለች አለው ።

፶፩ ወበዊአ ቤተ ኢኀደገ ይባእ ምስሌሁ ወኢመኑሂ ።

፶፩ ከቤት በገባ ጊዜም ከሱ ጋር ማንም ማን እንዳይገባ ከለከለ ።
ዘእንበለ ጴጥሮስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ ወአቡሃ ወእማ ለሕፃን ።
ከጴጥሮስ ከያዕቆብ ከዮሐንስ ከብላቴናዪቱ እናትና አባት በቀር ።

፶፪ ወኵሎሙ ይበክዩ ወያስቆቅዉ ።
፶፪ ሁሉም ያለቅሱላታል ያለቅሱላታል ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢትብክዩ ሕፃንሰ ኢሞተት አላ ትነውም ።
ጌታም ብላቴናይቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችምና አታልቅሱ አላቸው ።

፶፫ ወሠሐቅዎ [illegible]
[illegible]
[illegible] እስመ [illegible] ሞተት ።
እንደ ሞተች ዐውቀዋልና ።

፶፬ ወአውፅአ ኵሎ አፍአ ወአኀዛ እዴሃ ።
፶፬ ሰውን አስወጥቶ እጅዋን ይዞ አሥነሣት ።
ወጸውዓ ወይቤላ ተንሥኢ ወለትየ ።
ልጄ ሆይ ተነሺ ብሎ ጠራት ።

፶፭ ወገብአ ነፍሳ ።
፶፭ ያን ጊዜውንም ነፍሷ ገባች ።
ወተመውጠ መንፈሳ ላዕሌሃ ።
መንፈሷም ተመለሰ ።
ወተንሥአት ሶቤሃ ።
ያን ጊዜውንም ተነሣች ።
ወአዘዘ የሀብዋ ዘትበልዕ ።
የምትበላውን ስጧት አለ ።

፶፮ ወደንገፁ አቡሃ ወእማ ።
፶፮ አባት እናቷም አደነቁ ።
ወከልአሙ ኢይንግሩ ወኢለ መኑሂ ዘኮነ ።
የተደረገውን ለማንም ለማን እንዳይነግሩ ከለከላቸው ።

ዘከመ መሐርሙ እግዚእ ኢየሱስ ለሐዋርያት ወበእንተ ተፈንዎቶሙ ።

ምዕራፍ ፱ ።

፩ ወጸውዖሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ አርዳኢሁ ። ማቴ ፲፥፩ ማር ፫፥፲፭ ።

፩ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ጠራ ።
ወወሀቦሙ ኀይለ ወሥልጣነ ፤
ኃይል ሰጣቸው ።
ወአብሖሙ ላዕለ ኵሉ አጋንንት ፤
በአጋንንትም ላይ ሁሉ አሠለጠናቸው ።
ያሕይዉ ድውያነ ፤
ድውያንን ይፈውሱ ዘንድ ።

፪ ወፈነዎሙ ይስብኩ መንግሥተ እግዚአብሔር ፤

፪ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያስተምሩ ዘንድ ወይፈውሱ ድውያነ ።
ድውያንንም ይፈውሱ ዘንድ ላካቸው ።
ወኵሎሙ ሕሙማነ ።
የታመሙትንም ሁሉ ።

፫ ወይቤሎሙ ኢትንሥኡ ለፍኖት ወኢምንተ ። ማቴ ፲፥፱ ማር ፮፥፰ ።

፫ ለመንገድ ምንም ምን አትያዙ ።
ኢበትረ ። በትርም ቢሆን ።
ወኢጽፍነተ ። የስንቅ አቀማዳም ።
ወኢእክለ ። ስንቅም ።
ወኢወርቀ ፤ ወርቅም ቢሆን ።
ወኢክልኤተ ክዳናተ ፤
ሁለት ልብስም ቢሆን ።

፬ ወቤተ ኀበ ቦእክሙ ሀየ ንበሩ ።
፬ በገባችሁበትም ቤት ንሩ ፤
ወኢትፃኡ እምህየ እስከ ትወፅኡ ።
እስክትሄዱ ከዚያ አትውጡ ።

፭ ወዘሰ ኢተወከፈክሙ ወፂአክሙ እምይእቲ ሀገር ንግፉ ፀበለ እገሪክሙ ። ግብ ፲፫ ፶፩ ።

፭ የማይቀበላችሁን ግን ከዚያ አገር ወጥታችሁ የእግራችሁን ትቢያ አርግፉ ።
ከመ ይኩን ስምዐ ላዕሌሆሙ ፤
መረረጃ ይሆንባቸው ዘንድ ።

፮ ወወፂኦሙ ሐዋርያት አዑ አህጉረ አድያመ ።
፮ በወጡም ጊዜ በየሀገሩ አውራጃ ዞሩ ።
ወሰበኩ ወፈወሱ በኵለሄ ።
ድውይ እየፈወሱ ባራቱ ማዕዘን ዙረው አስተማሩ ።

በእንተ ሐልዮተ ሄሮድስ ላዕለ ኢየሱስ ።

፯ ወሰምዐ ሄሮድስ ንጉሥ ኵሎ ዘኮነ ። ማቴ ፲፬፥፩ ማር ፮፥፲፬ ።

፯ ንጉሡ ሄሮድስ የሆነውንም ሁሉ ሰማ ።
ዘከመ ገብረ ። ያደረገውን ፤
ወየኀጥእ በዘ ይብል ። የሚለውንም አጣ ።
እስመ ቦ እለ ይብሉ ዮሐንስ ተንሥአ እምውታን ።
ዮሐንስ ከሙታን ተነሣ የሚሉ አሉና ።

ወቦ እለ ይብሉ ኤልያስ አስተርአየ
ኤልያስ ተገለጠ ያሉም አሉና ።

፰ ወቦ እለ ይብሉ አሐዱ እምነቢያት ቀደምት ተንሥአ ።

[illegible] ቀድሞ የነበሩ ነቢያት አንዱ ተነሥቷል ያሉም አሉና ።

፱ ወይቤ ሄሮድስ ለዮሐንስሰ አነ መተርክዎ ርእሶ ።

፱ ሄሮድስ ግን የዮሐንስን ራሱን እኔ ቆርጬ [illegible] ዋለሁ ።
መኑ ፡ ውእቱ ዝንቱ ዘእሰምዕ በእንቲአሁ [illegible]
የሱን ነገር የምሰማ ይህ እንግዲህ ማነው አለ ።
ወፈቀደ ይርአዮ ።
ሊያየውም ይወድ ነበር ። ሐተታ ማቴዎስ ዮሐንስ መጥምቅ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ ይሆናል በግፍ አስገድየው ነበርና ስለዚህም ተአምራት ይደረግለት ይሆናል ብሏል ሉቃስ ለዮሐንስሰ አነ መተርክዎ ርእሶ አለ እንጂ [illegible] ነው [illegible] ቢሉ አይጣላም ነገር እንደ ማቴዎስ ነው [illegible] ሰዎች በዮሐንስ [illegible] ነበርና ደም [illegible] ይቀራሉ ብሎ ዮሐንስ መጥምቅ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ ይሆናል ብሏቸዋል ደግሞ [illegible] ካየ በኋላ ግን ለዮሐንስሰ አነ መተርክዎ ርእሶ ብሏል እንደ ሉቃስ ። እንዲሁም [illegible] በኋላ ሰይጣን አእምሮውን [illegible] አንድ ጊዜ እንዲህ አንድ ጊዜ እንዱን ይናገር ነበርና እንዲህ [illegible]

[illegible] ሐዋርያት [illegible]

፲ ወሶበ ገብኡ ሐዋርያት ነገርዎ ኵሎ ዘገብሩ ።

፲ ሐዋርያትም ተመልሰው ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት ።
ወነሥኦሙ ባሕቲቶሙ
ለብቻቸው ወሰዳቸው
ወተግኅሠ ።
[illegible] ሐቅለ ሀገር እንተ ትሰመይ ቤተ ሳይዳ ወደምትባል አገር ምድረ በዳ ሄደ ።

፲፩ ወአእሚሮሙ ሕዝብ ተለውዎ ።

፲፩ ሕዝቡም ባወቁ ጊዜ ተከተሉት ።

ወተቀበሎሙ ።
ሁሉንም ተቀበላቸው ።
ወነገሮሙ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርንም መንግሥት ነገራቸው ።
ወእለሂ ይፈቅዱ ይትፈወሱ አሕየዎሙ ።
ሊፈወሱ የወደዱትንም አዳናቸው ።

[illegible]

፲፪ ወተቀልቀለ ፀሐይ ።
[illegible] ፲፪ [illegible]
ወመጽኡ ፲ወ፪ አርዳኢሁ ወይቤልዎ [illegible]
[illegible]
ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው [illegible]
[illegible]
ወይቢቱ ውስተ አዕፃዳት ።
በየመንደሩ [illegible]
ወይኅሥሡ ዘይሴሰዩ ።
የሚበሉትንም ያገኙ ዘንድ ።
እስመ ሐቅል ውእቱ ኅቤ ሀሎነ ።

[illegible] ማቴዎስ ወእምድኅረ ብዙኅ ሰዓት [illegible] ወተቀልቀለ ፀሐይ እንደ ሉቃስ መገናኛው ዮሐንስ በተገናኘ ሲመሽ ማለት ነው [illegible] ማቴዎስ ፡ ሠዓር ሰብአ ማርቆስ [illegible] ዮሐንስ በተገናኘ አስናብቶ [illegible]

፲፫ ወይቤሎሙ [illegible]
አንትሙ [illegible]

፲፫ እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው አላቸው ።
ወይቤልዎ አልብነ ዝየ ዘእንበለ ኃምስ ኅብስት ወክልኤቲ ዓሣት ።
ከሁለት ዓሣና ከአምስት እንጀራ በቀር የለንም አሉት ።
እመ ኢሖርነ ንሣየጥ [illegible]
ለዚህ ሁሉ ሰው መብል [illegible]

፲፬ ወየአክሉ እደው ፶፻ ።

፲፬ ወንዶቹም አምስት ሺህ ያህል ይሆኑ ነበር ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ [illegible]
ምሙ በበ፶ ለለ ምርፋቄሙ ።
ጌታም ደቀ መዛሙርቱን [illegible] በየመቀመጫቸው አስቀምጧቸው አላቸው ።
፲፭ ወገብሩ ከማሁ ።

፲፭ እንዲሁ አደረጉ ።
ወረፈቁ ኵሎሙ ።
ሁሉንም አስቀመጡ

፲፮ ወነሥኦን ለኃምስ ኅብስት ወክልኤቲ ዓሣት ወነጸረ ሰማየ ።

፲፮ አምስቱን እንጀራ ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አየ ።
ወባረከ ። ባረከም ።
ወፈተተ ። [illegible] ቆረሰ ።
ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ያቅርቡ ለሰብእ ።
ለሰው ያቀርቡ ዘንድ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው ።

፲፯ ወአቅረቡ ወበልዑ ወጸግቡ ኵሎሙ ።
፲፯ ሁሉም በልተው ጠገቡ ።
ወዘአግንሡ ዘተርፈ ፍተታት መልአ ፲ተወ፪ተ መሳይምተ ምሉእን ።
ያነሡት የቀረው ቁራሽ ዐሥራ ሁለት መሶብ መላ ።

በእንተ እምነተ ጴጥሮስ ወበእንተ ትንቢት ዘሕማማት ።

፲፰ ወእንዘ ይጼሊ በባሕቲቱ ። ማቴ፡፲፮ ፡ ፲፫ ማር፡ ፰ ፡ ፳፯

፲፰ በብቻው ሲጸልይ ።
ወአርዳኢሁኒ ምስሌሁ ።
ደቀ መዛሙርቱ ከሱ ጋራ ሳለ
ተስእሎሙ ወይቤሎሙ መኑ ይብሉኒ ሰብእ ።
ሰው ማን ይለኛል ብሎ ጠየቃቸው ።

፲፱ ወተሰጥውዎ ወይቤልዎ ቦ እለ ይብሉከ ዮሐንስሃ መጥምቀ ።

፲፱ ዮሐንስ መጥምቅ ነው ይሉሃል ብለው መለሱለት ።
ወቦ እለ ይብሉከ ኤልያስሃ ።
ኤልያስ ነው የሚሉህም አሉ ።
ወቦ እለ ይብሉከ አሐዱ እምነቢያት ቀደምት ተንሥአ
ከቀደሙ ነቢያት አንዱ ተነሣ ያሉም አሉ አሉት ።

፳ ወእውሥአ ወይቤሎሙ አንትሙ መኑ ትብሉኒ ።

፳ እናንተ ማን ትሉኛላችሁ ።
ወተሰጥዎ ጴጥሮስ ።
ጴጥሮስ መለሰ ።
ወይቤሎ አንተ ውእቱ መሲሑ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ልጅ አንተ ነህ አለው ።

፳፩ ወገሠጾሙ ።
፳፩ ገሠጻቸው ።
ወከልዖሙ ኢይንግሩ ዘንተ ወኢለመኑሂ እምሰብእ ።
ይህን ለማንም ለማን እንዳይናገሩ ከለከላቸው ።

፳፪ ወይቤሎሙ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለእመሕያው ብዙኃ ያሐምምዎ ። ማቴ፡፲፯ ፡ ፳፩ ማር ፰ ፡ ፴፩

፳፪ ለሰው ልጅ ክርስቶስ ብዙ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው ።
ወያመክርዎ ረበናት ወሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ።
የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ጸሐፎችም በመከራ ይፈትኑት ዘንድ ።
ወይቀትልዎ ። ይገድሉታል ።
ወይትነሣእ በሣልስት ዕለት ።
በሦስተኛውም ቀን ይነሣል ።

በእንተ ክሒዶ ርእስ ለክርስቲያን ።

፳፫ ወይቤሎሙ ለኵሎሙ ዘይፈቅድ ይትልወኒ ይጽልእ ለነፍሱ ። ማቴ ፡ ፲፡፴፰ ፲፮ ፡ ፳፬ ፤ ማር፡ ፰ ፡ ፴፬ ሉቃ ፡ ፲፬ ፡ ፳፯ ዮሐ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ።

፳፫ በኋላዩ ሊከተለኝ የሻ ሰው ሰውነቱን ይካድ።
ወያጥብዕ ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ ወዘሎ ዕለተ ይትልወኒ ፤
ጨክኖ የሞቱን መስቀልም ይዞ ዕለት ዕለት ይከተለኝ ።

፳፬ ወዘሰ ይፈቅድ ያድኅና ለነፍሱ ይገድፋ ።
፳፬ ሰውነቱን ሊያድናት የወደደ ያጥፋታል ።
ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ ያድኅና ።
ስለኔ ሰውነቱን የጣላት ነፍሱን ያድናታል ።

፳፭ ወምንተ ይበቍዖ ለሰብእ ለእመ ኵሎ ዓለመ ረብሐ ወነፍሶ ኀጕለ ።

፳፭ በነፍሱ ከጠፋ ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ለሰው ምን ይረባዋል ።
ወለዘኒ ኀፈረኒ ። በኔ ያፈረ
ወኀፈረ ቃልየ ። በነገሬ ያፈረ ሰው ።

፳፮ የኃፍር ሎቱ ወልደ ዕጓለእመሕያው አመ ይመጽእ በስብሐቲሁ ወበስብሐተ አቡሁ ። ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፫ ማር፡ ፰ ፡ ፴፰

፳፮ በክብር ባባቱም ክብር በመጣ ጊዜ የሰው ልጅም ክርስቶስ ያፍረዋል ።
ወምስለ ቅዱሳን መላእክቲሁ ። ፪፡ጢሞ፡ ፪፡ ፲፪
በቅዱሳን መላእክት ምስጋናም በመጣ ጊዜ ።

፳፯ አማን አማን እብለክሙ ሀለዉ እምእለ ይቀውሙ ዝየ እለ ኢይጥዕምዎ ለሞት እስከ ይሬእይዎ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ።

፳፯ ከዚህ ቆመው ካሉት የእግዚአብሔርን መንግሥት እስኪያዩ ድረስ የማይሞቱ አሉ ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፳፰ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር አመ ሳምንት ዕለት ነሥኦሙ እግዚእ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ ወዓርገ ደብረ ከመ ይጼሊ ። ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ማር ፱ ፡ ፩ ።

፳፰ ከዚህ በኋላም በስምንተኛው ቀን ያዕቆብንና ጴጥሮስን ዮሐንስንም ይዟቸው ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ ።

፳፱ ወእንዘ ይጼሊ ተወለጠ ርዕየተ ገጹ ።
፳፱ ሲጸልይም የፊቱ መልክ ተለወጠ ።
ወአልባሲሁኒ ፃዕደወ ።
ልብሱም ነጭ ሆነ ።
ወበረቀ ከመ መብረቅ ።

ተብለጨለጨም ። ሐተታ ማቴዎስ ፮ ይላል ማርቆስ ስድስት ይላል ሉቃስ ስምንት አለ ።እንደ ምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ማቴዎስ ከወጡበትና ከወረዱበት አንዱን አውጥቶ ሰባት አለ ። ማርቆስ ሁለቱንም አውጥቶ ስድስት አለ ሉቃስ ሁለቱንም አግብቶ ስምንት አለ ። አንድም የማቴዎስ የሉቃስ አይለወጥም የማርቆስ የብተት ነው እኛ ስምንት ስንል አንድ ይላሉ ዐሥር ስንል ሦስት ዐሥራ ሦስት ስንል ስድስት ይላሉና አንድም ማቴዎስ አይለወጥም ማርቆስም አይለወጥም የብተት ነው ሉቃስ ስምንት ማለቱ ስባት ሲል ነው ። ንዒ ኀቤነ ለለሰሙነ እእምር ከመ ግብር ዘበእንተ ጾም ዓቢይ ከመ ውእቱ ሰመንቱ ሰሙን ውእቱ እንዲል ።

፴ ወናሁ መጽኡ ክልኤቱ ዕደው ።
፴ እነሆ ሁለት ሰዎች መጡ ።
እንዘ ይትናገሩ ምስሌሁ ።
ከሱም ጋራ ይነጋገሩ ነበር ።

፴፩ እሉ እሙንቱ ሙሴ ወኤልያስ ።
፴፩ እሊህ ሙሴ ኤልያስ ናቸው ።
እለ አስተርአዩ በስብሐት ።
በክብር የተገለጹ ።
ወነገሩ ስብሐቲሁ ዘሀለዎ ይኩን በኢየሩሳሌም ።
በኢየሩሳሌም ይደረግ ዘንድ ያለውን መከራውን የተናገሩ አፈወርቅ ይትባረክ እግዚአብሔር ዘሰመየ ሕማማተ ወልዱ ክብረ ወስብሐተ እንዲል ። እኛ የምንከብርበት ስለሆነ መከራውን ክብር ስብሐት ይለዋል ።
ወፀአቶሂ ።
ወደ ኢየሩሳሌም መውጣቱንም የተናገሩ ። አንድም ወደመስቀል መውጣቱን በኢየሩሳሌም ይደረግ ዘንድ ያለው ታምራቱን የተናገሩ እሊህ ናቸው ።

፴፪ ወፀአቶሂ ረከበ ጴጥሮስሃ ወእለሂ ምስሌሁ ክቡዳን አዕይንቲሆሙ በድቃስ ።

፴፪ ጌታ ከስዋሬው በተገለጸ ጊዜ ጴጥሮስን ወንድሞቹንም ደንግጠው አገኘ ። አንድም ኦውጣን አውጣን አሉ ስለ ወጡ ግን ጴጥሮስን ወንድሞቹን በጽኑ ዕንቅልፍ ተይዘው አገኛቸው ።
ወነቂሆሙ ርእዩ ስብሐቲሁ ።
በነቁም ጊዜ ክብሩን አዩ ።
ወእደውኒ ክልኤቱ እለ ይቀውሙ ምስሌሁ ።
ከሱ ጋራ ቁመው የነበሩትም ሁለቱ ሰዎች ።

፴፫ ወእምዝ ሶበ ፈቀዱ ይትሌለዩ እምኔሁ ይቤሎ ጴጥሮስ ለእግዚእ ኢየሱስ ሊቅ ንንበር ዝየ ።

፴፫ ከዚህ በኋላ ተለይተውት በሄዱ ጊዜ ጴጥሮስ ጌታን መምህር ከዚህ ልንኖር ይገባናል አለው ።
ወንግበር ሠለስተ ሰቃልወ ።
ሦስት ማደሪያም ልንሥራ ።

አሐዱ ለከ ።	አንዱን ላንተ ።
ወአሐደ ለሙሴ ።	አንዱን ለሙሴ
ወአሐደ ለኤልያስ ።	አንዱን ለኤልያስ ።

ወኢየአምር ዘይብል ።
የሚናገረውንም አያውቀውም ነበር ።

፴፬ ወዘንተ ብሂሎ ጸለሎሙ ደመና ።
፴፬ ይህንም ሲናገር ደመና ጋረዳቸው ።
ወቦአ ቦኡ ውስተ ደመና ፈርሁ ።
ከደመናው ውስጥ በገቡ ጊዜ ፈሩ ።

፴፭ ወመጽአ ቃል እምውስተ ደመና ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ ።

፴፭ ከደመናው የመረጥኩት ልጄ ይህ ነውና እሱን ስሙት የሚል ቃል ተሰማ ።

፴፮ ወመጺኦ ቃል ረከብዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ባሕቲቶ ።

፴፮ ድምፅ ከተሰማ በኋላ ጌታ ብቻውን ተገኘ ።
ወእሙንቱሰ አርመሙ ።
እነሱ ግን ዝም አሉ ።
ወኢነገሩ ለመኑሂ ዘርእዩ ወሰምዑ ይእተ አሚረ ።
በዚያን ጊዜ ያዩትን የሰሙትን ለማንም ለማን አል ተናገሩም ።

ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ ለዘያንገረግሮ ጋኔን ።

፴፯ ወእምዝ በሳኒታ ዕለት እንዘ ይወርዱ እምደብር ።

፴፯ ከዚህም በኋላ በነጋው ከተራራ ሲወርዱ ።
ተቀበልዎ ሕዝብ ብዙኃን ።
ብዙ ሰዎችም ተቀበሉት ።

፴፰ ወአውየወ አሐዱ ብእሲ በማእከለ ሕዝብ ።
ማቴ ፤ ፲፯ ፤ ፲፬ ማር ፱ ፤ ፲፯ ።

፴፰ አንድ ሰው በሕዝብ መካከል ጮኸ ።
ወይቤሎ ኦ ሊቅ ብቍዓኒ ።
መምህር ሆይ በጅ በለኝ ።
ረዓይ ሊተ ወልድየ ።
ልጄን እድንልኝ ።
እስመ አሐዱ ሊተ ውእቱ ።
ለኔ አንድ ነውና ።

፴፱ ወናሁ እኩይ ጋኔን የሐይዶ ።
፴፱ እነሆ ጋኔን ቀምቶኛል ።
ወያዌግቦ ።
ያስፈራራዋል ያስደነግጠዋል ።
ወታዌግበከሙ ዕለት እኪት ንንዲል ።

ወይነጽሖ ።	ይጥለዋል ።
ወያስተራግዖ ፤	ያራግጠዋል ።

ወያሴውና ፤ ያስለግገዋል ።
ወእም ዕፁብ የኃድጎ ቀጥቂጦ ።
በጭንቅ ቀጥቅጦ ይተወዋል ።

፵ ወአስተብቋዕክዎሙ ለአርዳኢከ ከመ ያውፅእዎ ።

፵ ደቀ መዛሙርትህንም ያወጡት ዘንድ ለመንኋቸው ።
ወስእንዎ ፈውሶቶ ወእውፅኦቶ ።
ግዳን ተሳናቸው ።

፵፩ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፵፩ ጌታም መለሰ ።
ወይቤ ኦትውልድ ዕሉት እንተ አልባቲ ሃይማኖት ።
እናንተ ሃይማኖት የሌላችሁ ዓመፀኛ ትውልድ ።
እስከ ማእዜኑ እሄሉ ምስሌክሙ ።
እስከ ፡ መቼ ከናንተ ጋራ እኖራለሁ ።
ወእስከ ማዕዜኑ እትዔገሠክሙ
እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ ብሎ ።
አምጽኦ ዝየ ለወልድከ ።
ልጅህን ወዲህ አምጣው አለው ።

፵፪ ወእንዘ ያመጽኦ ነጽሖ ጋኔን ።
፵፪ ሲያመጣው ጋኔኑ ጣለው ።
ወአስተራገፆ ። አራገጠው ።

፵፫ ወገሠጾ እግዚእ ኢየሱስ ለውእቱ ጋኔን እኩይ ።

፵፫ ጌታም ያን ክፉ ጋኔን ገሠጸው ።
ወአሕየዎ ለውእቱ ወልድ ።
ያንንም ልጅ አዳነው ።
ወመጠዎ ወአወፈዮ ለአቡሁ
ለአባቱም ሰጠው ።

በእንተ ዘተናገረ ኢየሱስ አቅዲሞ ነገረ ሞቱ ።

፵፬ ወአንከሩ ኵሎሙ እምዕበዩ ለእግዚአብሔር ።

፵፬ እግዚአብሔር ካደረገለት ታምራት የተነሣ ፤ እምዕበዮሙ ካደረገላቸው ታምራት በዕበዩ ባደረገለት ታምራት በዕበዮሙ ባደረገላቸው ታምራት በበዕበዩ በየተደረገለት ታምራት ። በበዕበዮሙ በየተደረገላቸው ታምራት ። በይነ ዕበዩ ስለ ተደረገለት ታምራት በይነ ዕበዮሙ ስለ አደረገላቸው ተአምራት አደነቁ ።
ወእንዘ እሙንቱ ያነክሩ በእንተ ፡ ኵሉ ዘገብረ እግዚእ ኢየሱስ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ አንትሙ ደይዎ ለዝንቱ ነገር ውስተ ልብክሙ ።
ጌታ ስለአደረገው ነገር ሁሉ እሱን ሲያደንቁ ደቀ መዛሙርቱን እናንተስ ይህን ነገር በልቡናችሁ አኑሩት አላቸው ።
እስመ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለእመሕያው ይግባእ ውስተ እደ ሰብእ ።
ለሰው ልጅ በሰው እጅ ይሰጥ ዘንድ አለውና ።

፵፭ ወኢለበውዎ ለዝንቱ ነገር ።
፵፭ ይህን ነገር አላስተዋሉትም ነበር ።
እስመ ስውር ውእቱ እምኔሆሙ ።
ይህ ነገር ተሰውሯቸው ነበርና ።
ከመ ኢይንሀኩ ።
እንዳያዝኑ ብእሲ ኢመዋቲ ዘአእመረ ሀኪከ እንዲል ።
ወይፈርህዎ ተጠይቆቶ በእንተ ዝንቱ ነገር ።
ስለዚህም ነገር እሱን መጠየቅ ይፈሩ ነበር ።

ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ትሕትና ወተአምኖተ ቢጽ ።

፵፮ ወሀለዩ በበይናቲሆሙ እንዘ ይብሉ መኑ የዐቢ እምኔሆሙ ። ማቴ፣፲፰ ፣ ፩ ማር ፱ ፣ ፴፫።

፵፮ ከርሳቸው ማንኛቸው እንዲበልጥ እርስ በርሳቸው አሰቡ ።

፵፯ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ዘይኄልዩ በልቦሙ ።

፵፯ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በልባቸው ያሰቡትን ዐውቆባቸው ።
ነሥአ ሕፃነ ወዓቀሞ በማዕከሎሙ ።
ሕፃን ወሰደ በመካከላቸው አቆመው ።

፵፰ ወይቤሎሙ ዘተወከፈ ዘመጠነዝ ሕፃን በስምየ ኪያየ ተወከፈ ።

፵፰ ይህን ሕፃን በስሜ የተቀበለ ሁሉ እኔን ተቀበለ ።
ወዘሰ ኪያየ ተወከፈ ተወከፎ ለዘፈነወኒ ።
እኔን የተቀበለም አባቴን ተቀበለ አላቸው ።
እስመ ዘአትሐተ ርእሶ እምኵሉ ውእቱ የዓቢ ።
ራሱን ያዋረደ ከሁሉ ይበልጣልና ።

፵፱ ወአውሥአ ዮሐንስ ።
፵፱ ዮሐንስ መለሰ ።
ወይቤሎ ሊቅ ቦ ዘርኢነ ፩ደ ብእሴ እንዘ ያወፅእ አጋንንተ በስምከ ወከላዕናሁ ።
መምህር ሆይ በስምህ ጋኔን ሲያወጣ አንድ ሰው አግኝተን የከለከልነው አለ አለው ።
እስመ ኢተለወከ ምስሌነ ።
ከኛ ጋራ አልተከተለህምና ።

፶ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢትክልዕዎ ።

፶ ጌታም አትከልክሉት አላቸው ።
እስመ እምከመ ኢኮነ ዕድውክሙ ቢጽክሙ ዘምስሌክሙ ውእቱ ።
ባለጋራችሁ ካልሆነ ከናንተ ጋራ ነው ፣

ዘከመ ተሰደ ኢየሱስ እምሰማርያ ።

፶፩ ወተፈጸሞ መዋዕለ ዕርገቱ እንጸረ ገጾ ለሐዊር መንገለ ገጸ ኢየሩሳሌም ።

፶፩ ወደ ደብረ ታቦር የሚ ወጣ በት በኤፍሬም ዕጣ የሚኖርበት ቀን በተፈጸመ ጊዜ ። አንድም ወደ ኢየሩሳሌም ወደመስቀል የሚወጣበት ቀን በደረሰ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን መለሰ ።

፶፪ ወፈነወ ሐዋርያተ ቅድመ ገጹ እለ ይዜንዉ ።

፶፪ መጥን አሰናዱ ብሎ ሐዋርያትን በፊቱ ላከ
ወሐዊሮሙ ቦኡ ሀገረ ሳምር ።
ሄደው ወደ ሳምራውያን አገር ገቡ ።
ከመ ያስተዳልዉ ።
መጥን ያሰናዱለት ዘንድ ።

፶፫ ወኢተወከፍዎሙ ።
፶፫ አልተቀበሏቸውም ።
እስመ ርሕው ውሑሉፍ ገጹ ለኢየሩሳሌም ።
ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም አቅንቶ ነበርና ፤ ሐተታ የፍቅር ነው ምነው በኛ በኩል ያልመጣ ብለው ።

፶፬ ወርእዮሙ አርዳኢሁ ያዕቆብ ወዮሐንስ ዘንተ ።

፶፬ ደቀ መዛርቶቹ ያዕቆብና ዮሐንስ ይኸን አይተው ።
ይቤልዎ ሊቅ ንፈቅድ ትበል ይረድ እሳት እምሰማይ ወያጥፍኦሙ በከመ ገብረ ኤልያስ ።
መምህር ሆይ ኤልያስ ሁለት ጊዜ እሳት ከሰማይ አውርዶ አምሳ አምሳውን ጭፍራ ከነአለቆቻቸው እንደአቃጠላቸው እሳት ከሰማይ እውርደህ ልታቃጥላቸው እንወዳለን አሉት ።

፶፭ ወተመይጠ ገሠጾሙ እግዚእ እየሱስ ።
፶፭ ተመልሶ ተቆጣቸው ። የቦታም ከመዓት ወደምኅረት ተመልሶ ።
ወይቤሎሙ ኢያእመርክሙኑ መጠና ለነፍስክሙ።
የሰውነታችሁን መጠን አታውቁምን ማለት እኔ ብታገኟችሁ ነው እንጂ እናንተስ ከነዚያን ልዩ ናችሁ አላቸው ። አንድም ዘአይ መንፈስ አንትሙ የሚል አብነት ይገኛል የማን ሀብት ወገን ናችሁ ሀብተ ርትዕ ያለው ኤልያስ ሁለት ጊዜ እሳት ከሰማይ አውርዶ ሁለቱን አለቆች ካምሳ ካምሳ ጭፍራ ጋራ አስፈጃቸው ። እናንተማ ሀብተ ትሩፋት ያለኝ የኔ ወገን አይደላችሁምን። አንድም የማን መምህር ደቀ መዛሙርት ናችሁ ሀብተ ርትዕ ያለው የኤልያስ ደቀ መዝሙር ኤልሳዕ ሁለት ድባት እሥነሥቶ አርባ ሁለት ሕፃናት አስፈጀ ። እናንተ ሀብተ ትሩፋት ያለኝ የኔ ደቀ መዛሙርት አይደላችሁምን ።

፶፮ እስመ ኢመጽአ ወልደ ዕጓለ እምሕያው ከመ ያጥፍዕ ነፍሳተ ሰብእ ዘእንበለ ከመ ያድኅን ዘተኀጕለ ። ማ፡ቴ፲፰፡፲፩ ማር፡፱፡፴፪ ።

፶፮ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ሊያድን ነው እንጂ ሊያጠፋ አልመጣምና ።
ወሖሩ ካልዕተ ሀገረ ።
ወደሌላም አገር ሄዱ ።

ዘከመ ይደሉ በዓይ ተሊዎተ ኢየሱስ ።

፶፯ ወእምዝ እንዘ የሐውሩ በፍኖት ይቤሎ አሐዱ ሊቅ እትሉከኑ ኀበ ሖርከ ።

፶፯ ከዚህ በኋላ ሲሄዱ አንድ ሰው መምህር ሆይ ልከተልህን አለው ።

፶፰ ወይቤሎ ኢየሱስ ለቆናጽልኒ ግቡብ ቦሙ ማቴ ፰፡፳ ።

፶፰ ጌታም ለቀበሮዎች ጕድጓድ አላቸው ።
ወለአዕዋፈ ሰማይኒ ምጽላል ቦሙ ።
ለዎፎችም ማረፊያ አላቸው ።
ለወልደ ዕጓለ እመሕያውሰ አልቦቱ ኀበ ያሰምክ ርእሶ ።
ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ግን ራሱን ለሚያስጠጋበት የለውም አለው ።

፶፱ ወይቤሎ ካልዑኒ እትሉከኑ እግዚኦ ።
፶፱ ሌላውም እቤቱ ልከተልህን አለው ።
ወባሕቱ አብሐኒ እሑር ቅድመ እቅብሮ ለአቡየ ።
ነገር ግን አስቀድሜ ሄጄ አባቴን እቀብር ዘንድ አሰናብተኝ አለው ።

፷ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ኅድጎሙ ለምውታን ይቅብሩ ምውታኒሆሙ ።

፷ ጌታም ሙታንን ተዋቸው ሙታናቸውን ይቅበሩ ።
ወአንተሰ ሑር ወሰብክ መንግሥተ እግዚአብሔር።
አንተስ ሂደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት አስተምር አለው

፷፩ ወይቤሎ ባልሱኒ እትሉከኑ እግዚኦ ።
፷፩ ሦስተኛው ሌላውም ልከተልህን አለው፤
ወባሕቱ አብሐኒ እሑር እሥራዕ ዙሎ ሰብአ ቤትየ ወእምጽእ ።
ነገር ግን ቤተ ሰዎቼን እሠራ ዘንድ ማለት በዚህ ዋሉ በዚህ እደሩ ብዬ ልምጣ ። አንድም እሰነአል ይላል ተሰናብቼ ልምጣ አለው ።

፷፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አልቦ ዘይአኀዝ ዕርፈ ወየሐርስ ድኅሬተ ወይክውን ድልወ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ።

፷፪ ጌታም ዕርፍ ይዞ ወደኋላው የሚያርስ የለም እስው ከመነኑም በኋላ ወደ ዓለም የሚመለስ የለም ።
እስመ ርትዕት ይእቲ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር መንግሥት የቀናች ናት ማለት ወደፊት ናት

በእንተ ተፈንዎት ዘሐዋርያት ቀዳማውያን ።

ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወእምዝ አርአየ እግዚእነ ካልዓነ ሰብአ ።
፩ ፸ ኃረየም ይላል ። ከዚህም በኋላ ጌታችን ሰብዓ አርድዕትን መረጠ ።
ወፈነዎሙ በበክልኤቱ ቅድመ ገጹ ፤
ሁለት ሁለቱንም በፊቱ ላካቸው ፤
ውስተ ኵሉ አህጉር ።
በየሀገሩ ሁሉ ፤
ወበሐውርት ኀበ ሀለዎ ይባእ ፤
ይገባበት ዘንድ በያለውም አውራጃ ሁሉ ።
ኀበ ሀለዎሙ ይባእሙ ፤
ጌታ ይገባቸው ዘንድ ወዳላቸው አህጉር ፣ ኀበ ሀለዎሙ ይባኡ ፣ ሐዋርያት ይገቡባቸው ዘንድ ወዳላቸው ።
ሀበ ሀለዎሙ ይባዕዎሙ ።
ሐዋርያት ይገቡባቸው ዘንድ ወዳለው አህጉር ።
፪ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ማዕረሩሰ ብዙኅ ። ማቴ፡፱፡፴ ።
፪ ጌታም መከሩ ብዙ ነው አላቸው ።
ወገባሩ ኅዳጥ ።
ሠራተኞች ግን ጥቂት ናቸው ።
ሰእልዎ እንከ ለበዓለ ማዕረር ከመ ይፀሰክ ወይፈኑ ገባረ ለማዕረሩ ።
ስመከሩ ሠራተኞችን ያክል ዘንድ ባለመከሩን ለምኑት አላቸው ።

፫ ሑሩ ናሁ እፌንወክሙ ከመ አባግዐ ማዕከለ ተኵላት ። ማቴ፡፲፡፲፮ ።
፫ እነሆ እንደ በግ ተኵላ ወዳለበት እልካችኋለሁና ሂዱ አላቸው ።
፬ ወኢትጹሩ ቍናማተ ፤
፬ ከረጢት አትያዙ ።
ወኢጽፍነተ ፣ ስልቻም ።
ወኢአሣዕነ ። ጫማም ።
ወኢምንተኒ ።
ምንም ምን አትያዙ ።
ወኢተአምኁ ወኢመነሂ በፍኖት ።
በመንገድ ለማንም ለማን ሰላምታ አትስጡ

፭ ወኀበ በጽሕክሙ ቤተ ቅድሙ በሉ ሰላም ለሰብአ ዝንቱ ቤት ።

፭ ከገባችሁበት ቤት አስቀድማችሁ ለዚህ ቤት ሰዎች ሰላም በሉ ።

፮ ወእመቦ ሀየ ወልደ ሰላም ያዕርፍ ሰላምክሙ ላዕሌሁ ።

፮ ከዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር ሰላማችሁ ይደርበት ።
ወእመ አኮሰ ይግባእ ሰላምክሙ ላዕሌክሙ ።
ባይኖርም ሰላማችሁ ወደእናንት ይመለስ ።

፯ ወውእተ ቤተ ንበሩ ። ዘዳግ፡፳፬፡፲፬፡ማቴ፡ ፩ ፡፲፪ ፩ጢሞ፡፭ ፡ ፲፰ ።

፯ ከገባችሁበት ቤት ኑሩ ።
ብልዑ ወስትዩ ዘእምኀቤሆሙ ።
በርሳቸው ዘንድ የተገኘውን ብሉ ጠጡ ።
እስመ ይደልዎ አስቡ ለዘይትቀነይ ።
ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋልና
ወኢትትፋለሱ እምቤት ውስተ ቤት ።
ካንዱ ቤት ወደአንዱ ቤት አትሂዱ ።

፰ ወሀገረኒ እንተ ኀበ ቦእክሙ ወተወክፉክሙ ሰብእ ይእቲ ሀገር ።

፰ ከገባችሁበት ከተቀበሏችሁም አገር ።
ብልዑ ዘአቅረቡ ለክሙ ።
ያቀረቡላችሁን ብሉ ።

፱ ወፈውሱ ድዉያን እለ ውስቴታ ።
፱ ያሉትን ድውያንንም ፈውሱ ።
ወበልዎሙ ቀርበት መንግሥተ እግዚአብሔር ኀቤክሙ ።
የእግዚአብሔር መንግሥትም ወደናንተ ቀርባለች በሏቸው ።

፲ ወእየኒ ሀገረ ኀበ ቦእከሙ ወኢተወከፉክሙ ሰብአ ይእቲ ሀገር ወፂእክሙ ውስተ መርኅባ ።

፲ ከገባችሁበት ካልተቀበሏችሁ አገር ግን ወደ ዐደባባይ ወጥታችሁ ።
ንግፉ ፀበለ እገሪክሙ እንዘ ትብሉ ።
የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ ።

፲፩ ወፀበለክሙኒ ዘተለወነ እምሀገርክሙ ነገፍ ለክሙ ።

፲፩ ከሀገራችሁ የተጣበቀብንን ትቢያ ስንኳን አራገፍንላችሁ ብላችሁ ።
ወባሕቱ ዘንተ አእምሩ ከመ ቀርበት መንግሥተ እግዚአብሔር ላዕሌክሙ ።

ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግሥት ለእናንተ እንደ ቀረበች ይህንም ዕወቁ ።

፲፪ እብለክሙ ሰዶም ትኄይስ ወትረክብ ማህለ ፈድፋደ እምይእቲ ሀገር በዕለተ ደይን ፤

፲፪ ከዚያችም አገር ይልቅ በፍርድ ቀን ሰዶም ትሻላለች ይቅርታንም ታገኛለች ብየ እነ ግራችኋለሁ ።

፲፫ አሌ ለኪ ኮራዚ ። ማቴ ፲፩፡፳፩ ።
፲፫ ኮራዚ ሆይ ወዮልሽ ፤
አሌ ለኪ ቤተ ሳይዳ ፤
ቤተ ሳይዳ ሆይ ወዮልሽ ፤
ሶበሰ በጢሮስ ወበሲዶና ተገብረ ኃይል ዘተገብረ በውስቴትክን እምትካት ፤
በናንተ የተደረገው ኃይል በሲዶናና በጢሮስ ተደ ርጎስ ቢሆን ።
ሠቀ እምለብሱ ። ማቅ በለበሱ ነበር ።

ወውስተ ሐመድ እምነበሩ ፤ ወእምነስሑ ።
በአመድ በተቀመጡ ንስሐም በገቡ ነበር ።

፲፬ ወባሕቱ ጢሮስ ወሲዶና ይረክባ ማህለ ፈድፋደ እምኔክን በዕለተ ደይን ፤

፲፬ ነገር ግን በፍርድ ቀን ከናንተ ይልቅ ጢሮስና ሲዶና ይቅርታን ያገኛሉ ።

፲፭ ወአንቲኒ ቅፍርናሆም እመ ተለአልኪ እስከ ሰማይ ሀለወኪ ትረዲ ውስተ ሲኦል ።

፲፭ አንች ቅፍርናሆም እስከ ሰማይ ከፍ ከፍ ብትዪ እስከ ሲኦል ትወርጃለሽ ።

፲፮ ዘኪያከሙ ሰምዓ ኪያየ ሰምዓ ማቴ.፲፡፵ ዮሐ.፲፫፡ ፳ ።

፲፮ እናንተን የሰማ እኔን ሰማ ።
ወዘለክሙ እበየ ሊተ አበየ ።
እናንተን እምቢ ያለ እኔን እምቢ አለ ።
ወዘሊተ አበየ አበዮ ለዘፈነ ወኒ ።
እኔን እምቢ ያለ የላከኝን አባቴን እምቢ አለ ።
ወዘሊተ ሰምዓ ሰምዖ ለዘፈነወኒ ።
እኔን የሰማ የላከኝን አባቴንም ሰማ ።

ዘከመ ተመይጡ እምዘተፈነዉ ።

፲፯ ወተመይጡ እልኩቱ ሰብእ እለ ተፈነዉ እንዘ ይትፌሥሑ ወይቤሉ እግዚኦ አጋንንትሂ ገረሩ ለነ በስምከ ።

፲፯ እሊህም ሰብዓ ሁለቱ አርድዕት አቤቱ አጋንንት በስምህ ተገዙልን እያሉ ደስ ብሏቸው ተመለሱ ።

፲፰ ወይቤሎሙ ርኢክዎ ለሰይጣን ከመ መብረቅ ወድቀ እምሰማይ ።

፲፰ ሰይጣንን ከሰማይ እንደ ወደቀ መብረቅ አየሁት፤ ሐተታ መብረቅ ከተበተነ በኋላ ሥራ እን ዳይሠራ ሰይጣንም በገዳም በምስቱ አርእስተ ኃጣ ውአ ድል ከነሳሁት በኋላ ሥራ እንዳይሠራ ዓው ቃለሁ ።

፲፱ ወናሁ ወሀብኩክሙ ሥልጣነ ትኪዱ ዲበ ዓቃርብት ወዲበ አራዊተ ምድር ወዲበ ኵሉ ኃይለ ጸላዒ ።

፲፱ በአባብና በጊንጥ በጸላትም ሁሉ ኃይል ላይ ትሔዱ ዘንድ ማለት ሊቃነ አጋንንት እኩያት ፍት ወታት ኃጣውእን ድል ትነሡ ዘንድ እነሆ ሥልጣን ሰጠኋችሁ ።
ወአልቦ ዘይነክየክሙ ።
የሚያገኛችሁ ጉዳት የለም ።

፳ ወባሕቱ በዝስ ኢትትፌሥሑ እስመ አጋ ንንት ይገንዩ ለክሙ ።

፳ ነገር ግን አጋንንት ስለተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ ።
ሐተታ በዚህ ደስ አይበላችሁ ።
በእንተ እለ ይመጽኡ ይትፌወሱ ።
የሚደረግ ተአምራት አለና ፤
እስመ ገቢረ ተአምራት መንከራት ኢይክል ያድ ኅን እምኵነኔ ገሃነም እንዲል ።
ተፌሥሑ ባሕቱ እስመ ተጽሕፉ አስማቲክሙ በሰ ማያት ።
ነገር ግን ስማችሁ በሰማይ ተጽፏልና ማለት በልበ እግዚአብሔር ታውቋልና ፤ ስለዚህ ደስ ይበላችሁ ።

በእንተ ድኅነት ።

፳፩ ወበይእቲ ሰዓት ተፈሥሐ እግዚእ ኢየሱስ በመንፈሱ ቅዱስ ።

፳፩ በዚያን ጊዜም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ደስ አለው ።
ወይቤ አአምነከ አባ እግዚእ ሰማይ ወምድር ዘኃ ባዕኮ ለዝንቱ እምጠቢባን ወእምለባውያን ወከሠ ትኮ ለሕፃናት ።
ይህን ከብልሃተኞችና ካስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃ ናት የገለጽኸው የሰማይና የምድር ጌታ አባቴ ሆይ አመሰግንሃለሁ ።
እወ አባ እስመ ከማሁ ኮነ ሥምረትከ በቅድሜከ ።
አዎን አባት ሆይ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሁናለችና።

፳፪ ወተመይጠ ኀበ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ ኵሉ ተውህበ ሊተ እምኀበ አቡየ።ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯።

፳፪ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ ሁሉ ከባቴ ተሰጠኝ አላቸው ።

ወእልቦ ዘየአምሮ ለወልድ ከመ መኑ ውእቱ ወልድ ዘእንበለ አብ ።
ወልድን ያለ አብ ማን እንደሆነ የሚያቀው የለም ።
ወእልቦ ዘየአምሮ ለአብ ከመ መኑ ውእቱ አብ ዘእንበለ ወልድ ።
አብንስ ያለወልድ የሚያውቀው ማነው ።
ወለዘፈቀደ ወልድ ይክሥት ሎቱ ።
ወልድ ማን ለወደደው ይገለጥለታል ።

፳፫ ወተመይጠ ኀበ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ እንተ ባሕቲቶሙ ብፁዓት አዕይንት እለ ይሬእያ ዘትሬእዩ አንትሙ ። ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮ ።

፳፫ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ እናንተ የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች የተመሰገኑ ናቸው ።

፳፬ እብለክሙ ከመ ብዙኃን ነቢያት ወነገሥት ፈተዉ ይርአዩ አንትሙ ዘትሬእዩ ወኢርአዩ ።

፳፬ ብዙ ነገሥታትና ነቢያት እናንት የምታዩትን ሊያዩ እንደወደዱ እንዳላዩ ።
ወይስምዑ ዘትሰምዑ አንትሙ ወኢሰምዑ ።
እናንተ የምትሰሙትንም ሊሰሙ እንደወደዱ እንዳልሰሙ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፳፭ ወእምዝ ተንሥአ አሐዱ ጸሐፊ ሀገር ያመክሮ ። ማቴ ፡ ፳ ፡ ፪ ፴፭ ማር ፡ ፲፪ ፡ ፳፰ ።

፳፭ ከዚህ በኋላ አንድ ያገር ጸሐፊ ሊፈትነው ተነሣ ።
ወይቤሎ ኦ ሊቅ ምንተ ገቢርየ እወርስ ሕይወተ ዘለዓለም ።
መምህር ሆይ ምን ሥራ ሠርቼ የዘለዓለም ሕይወት እወርሳለሁ አለው ።

፳፮ ወይቤሎ ውስተ ኦሪትከ ምንት ጽሑፍ ።
፳፮ በኦሪትህ የተጻፈው ምንድር ነው ።
ወእፎ ታነብብ እንዴትስ ታነባለህ አለው ።

፳፯ ወአውሥአ ወይቤሎ ዘዳ ፡ ፮ ፡ ፭ ።
፳፯ እሱም እንዲህ ብሎ መለሰ ።
አፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ልብከ ።
አምላክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ ውደደው ።
ወበኵሉ ነፍስከ ።
በፍጹም ስውነትህ ።
ወበኵሉ ኃይልከ ።
በፍጹም ኃይልህም ።
ወበኵሉ ሕሊናከ ፤
ባሳብህም ሁሉ ።
ወአፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ ።
ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ያለውም ነው አለው

፳፰ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ሠናየ ተሠጠውከ
፳፰ ጌታም መልካም መለስህ ፤
ከማሁ ግበር ወተሐዩ ።
እንዲሁ አድርግ ትድንማለህ አለው ።

፳፱ ወፈቀደ ከመ ያጽድቅ ርእሶ ወይመንን ቢጾ ወይቤሎ ለእግዚእ ኢየሱስ መኑ ውእቱ ቢጽየ ።

፳፱ ራሱን ሊያከብር ባልንጀራውንም ሊያዋርድ ወዶ እንደኔ ያለ ማነው አለ ።

በእንተ ተራኅርኆተ ሳምራዊ ወተሠጠዎ እግዚእ ኢየሱስ ።

፴ ወይቤሎ አሐዱ ብእሲ እንዘ ይወርድ እምኢየሩሳሌም ለኢያሪኮ ።
ወፈቀደ ከመ ያጽድቅ ርእሶ ወይመንን ቢጾ ብሎ ነበርና ።

፴ ጌታም መለሰለት አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲወርድ ።
ረክብዎ ፈያት ።
ወንበዴዎች አግኝተውት ።

ዘበጥዎ ፤	ደበደቡት ።
ወፈቅዕዎ ፤	ገምሰው ።
ወአቍሰልዎ ፤	አቍስለው ።
ወሰለብዎ ፤	ልብሱን ገፈው ።
ወገደፍዎ ወሐለፉ ፤	ጥለውት ሄዱ ።
ወአልጸቀ ይሙት ፤	ሊሞት ቀረበ ።

፴፩ ወተዳደቀ አሐዱ ካህን እንዘ ይወርድ ይእተ ፍኖተ ።

፴፩ በዚያን መንገድ ሲሄድ አንድ ካህን አገኘው ።
ወርእዮ ተዓደወ ወኀለፈ ።
አይቶም አልፎት ሄደ ።

፴፪ ወከማሁ ሌዋዊኒ መጽአ ኀበ ውእቱ መካን ወረከቦ ከመ ቀዳማዊ ።

፴፪ የሌዊ ወገን ሰውም እንዲሁ አገኘው ።
ወርእዮሂ ተዓደወ ወኀለፈ ።
አይቶም ዝም ብሎ ሄደ ። ወከማሁ ባለው ወከመ ገጽ የሚል አብነት ይገኛል ። ከመ ቀዳሚ ማለት ነው ።

፴፫ ወረከቦ አሐዱ ሳምራዊ እንዘ የሐውር ይእተ ፍኖተ ።
ሳምራዊም በዚያ መንገድ ሲሄድ አገኘው ።
ወርእዮ ወምሕሮ ።
አይቶም አዘነለት ።

፴፬ ወቀርበ ኀቤሁ ወሦጠ ወይነ ወቅብዓ ውስተ ቍስሊሁ ።

፴፬ ወደሱ ቀርቦ በቍስሉ ወይንና ዘይት አፈሰሰበት ። ሐተታ ዘይት ያለመልማል ወይን ያደርቃልና ።

ወፀእኖ ዲበ አድጉ ወወሰዶ ኀበ ዓቃቤ ቤት ነግድ።
በአህያው ላይ አስቀምጦ ወደ መንደረኛው ይዞት ሄደ ።
ከመ ይፈውሶ ።   ያድነው ዘንድ ።
ወእስተሐመመ በግብሩ ።
የሚያድንበትን አሰበ ፣

፴፭ ወበሳኒታ አውፅአ ክልኤተ ዲናረ ወወሀቦ ለዓቃቤ ቤተ ነግድ

፴፭ በነጋውም ሁለት ድሪም አውጥቶ ለመንደረኛው ሰጠው ።
ወይቤሎ ፈውሶ ሊተ በዝንቱ ፤
በዚህ አድንልኝ አለው ።
ወእመቦ ዘአስተዋፃዕከ ሎቱ ዘይበዝኅ እምዝ እፈድየከ አነ እመ ግብአትየ ።
ከዚህም የሚበዛ ስለሱ ያወጣኸው ገንዘብ ቢኖር በተመልስኩ ጊዜ እከፍልሃለሁ አለው ።

፴፮ መኑ እንከ እምእሉ ፫ቱ ዘይከውኖ ቢጾ ለዘዘበጥዎ ፈያት ።

፴፮ ወንበዴዎች ለደበደቡት ለዚህ ከሦስቱ ወዳጅ የሆነው ማነው አለው ።
ወይቤሎ ዘገብረ ምሕረተ ላዕሌሁ ።
ምሕረት ያደረገለት ሳምራዊ ነው አለው ።

፴፯ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ሑርኬ አንተኒ ግበር ከማሁ ።

፴፯ ጌታም አንተም ሄደህ እንዲሁ አድርግ አለው ።
ወተሐዩ ።
ትድን ዘንድ ድኅነት ታገኝ ዘንድ ። አንድም ወተሠጥዎ ብለህ መልስ አዳምን ከልዕልና ወደ ትሕትና ሲሄድ አግኝተውት አጋንንት አስተው ልጅነቱን አስወስደውበት ሄዱ አንድም በአዳም የሁሉን መናገር ነው ። ወአልጸቀ ይሙት በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም ተፈረደበት ። ወተዳደቆ ። መልከ ጼዴቅ በዚህ ዓለም አገኘው በጸለየው ጸሎት ባቀረበው መሥዋዕት አላዳነውም ። ወከማሁ አሮን በዚህ ዓለም አገኘው አላዳነውም አንድም አሐዱ ካህን ሙሴ ፣ ሌዋዊ አሮን ።
አንድም አሐዱ ካህን። አሮን ሌዋዊ ከአሮን እስከ ሐና እስከ ቀያፋ ያሉ ካህናት በጸለዩት ጸሎት ባቀረቡት መሥዋዕት አለማማለዳቸውን መናገር ነው ወረከቦ አሐዱ ሳምራዊ ጌታ በዚህ ዓለም አገኘው ሳምራዊ ዐቃቤ ሀገር እንደሆነ ጌታም ዓቃቤ ልቦና ነውና የሳምራዊ ትውልዱ ከሕዝብ ከአሕዛብ እንደሆነ የጌታም ትውልዱ ከሕዝብ ከአሕዛብ ነውና ። ወርእዮ ፣ በዓይነ ምሕረት አየው።ወምሕሮ አዘነለት ። ወቀርበ ኀቤሁ ፣ ባሕርዩን ባሕርይ አደረገለት በመስቀል ተሰቀለለት።ወሦጠ ወይነ ወቅብዓ ። ልጅነትን ሥጋውን ደሙን ሰጠው።ወወሰዶ ከጣዖት ከኃጢአት ፈልሶ የመጣውን ለሚያስተምሩ ለመምህራን ሰጠው ፣ ከመ ይፈውሶ ፣ እስተምረው ያድኑለት ዘንድ ፣ ወፀእኖ በአህያ ተቀመጠለት ተዋረደለት ፣ ወእስተሐመመ የሚያድንበትን አሰበለት ፣ ወበሳኒታ የዕርገት ሳኒታ ጰራቅሊጦስ ነው ፣ የጰራቅሊጦስ ብሉይና ሐዲስ አወጣጥቶ ከጣዖት ከኃጢአት ፈልሶ የመጣውን ለሚያስተምሩ መምህራን ሰጠለት ፣ ወይቤሎ ፈውስ በዚህ መከራችሁ አስተምራችሁ አድኑልኝ አላቸው ። ወእመቦ ከዚህም ሌላ ድርሰት ደርሳችሁ ተግሳጽ ጽፋችሁ ያስተማራችሁት ቢኖር በመጣሁ ጊዜ ዋጋችሁን እሰጣችኋለሁ ፣ መኑ እንከ እምእሉ ፣ አጋንንት ልጅነቱን ላስወሰዱበት ለአዳም ከሦስቱ በጐ ሥራ የሠራለት ማነው አለው ፣ ወይቤ ዘገብረ ምሕረተ ላዕሌሁ ፣ አንተ ነህ አለው ፣ ወይቤ ሑር አንተኒ ግበር ከማሁ ፣ እንኪያስ አንተም እኔን አብነት አድርገህ ሥራ ብትሠራ ፣ ወተሐዩ ። ትድናለህ ።

በእንተ ማርያ ወማርታ ።

፴፰ ወእምዝ ሖዊሮሙ ቦኡ አሐተ ሀገረ።
፴፰ ከዚህ በኋላ ሄደው ወደአንድ ሀገር ገቡ።
ወተቀበለቶ አሐቲ ብእሲት ውስተ ቤት እንተ ስማ ማርታ ፣
ማርታ የምትባል ሴት በቤቷ ተቀበለችው ።

፴፱ ወሰመ እኅታ ማርያ ።
፴፱ እኅቷ ማርያ ትባላለች ።
እንተ ነበረት ኀበ እገሪሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ከጌታ ዘንድ ስትማር ትውል ነበር ።
ወትሰምዕ ቃሎ ።
ወንጌልን ትሰማ ነበር ።

፵ ወማርታስ ትሰርሕ በእስተዳልዎ ብዙኃ፡
፵ ማርታ ግን በብዙ ማዘጋጀት ብዙ ትደክም ነበር ።
ወቆመት ወትቤሎ እግዚእየ ኢያጽሕቀከኑ ግብርየ ዘተኃድገኒ እኅትየ ባሕቲትየ እንዘ እስተዳሉ ።
ቆማ እኅቴ ብቻየን የምትተወኝ ድካሜ አያሳዝንህምን ።
በላኬ ትርድእኒ ።
ትረዳኝ ዘንድ እዘዝልኝ አለችው ።

፵፩ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ማርታ ማርታ ለምንት ትሠርሒ ብዙኃ ታስተዳልዊ ።

፵፩ ለዕብራውያን ደጊመ ቃል ልማዳቸው ነው እብርሃም እብርሃም እልዓዛር እልዓዛር ስምዖን ስምዖን እንዲል ማርታ ማርታ ሆይ ታዘጋጂ ዘንድ ስምን ብዙ ትደክሚያለሽ ።
ወኅዳጥ የአክል ።   አንድ እንጀራ ይበቃል ።

ወእመ አኮ ለሐቲ መክፈልት ።
ዘሃይ እንጀራ ካይገኝ ካሚስ ይበቃል መክፈልትን ይዞ ። አንድም ኅዳጥ የእህል ገሚስ ይበቃል [illegible] ይዞ ።

ወእመ [illegible] መክፈልት [illegible]
አንድ እንጀራ ይበቃል ። ለሐቲን ይዞ ።
[illegible] ከፈልት [illegible]
[illegible] በታው ተኩስ [illegible]

ማርያም [illegible] የሚቆማት የሌለ ትምህርትን መረጠች
[illegible] የማትርቀውን ።

[illegible] ፲፩ ።

በእንተ ጸሎት ክርስቲያናዊት ።

፩ ወእምዝ ጸለየ በአሐቲ መካን ።
፪ ከዚህ በኋላ ባንድ [illegible] ጸለየ ።

ወፈጺሞ ጸሎተ ይቤሉ አሐዱ እምአርዳኢሁ እግዚኦ መሐረነ ጸሎተ በከመ መሐሮሙ ዮሐንስ ለአርዳኢሁ ።

ጸሎቱን ሲፈጽም ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አቤቱ ዮሐንስ ለደቀ መዛሙርት እንዳስተማረ [illegible] ልየው ጸሎት አስተምረን አለው [illegible] ምን ያስተምር ነበር ቢሉ ዳግም ሕግን ። አንድም [illegible] [illegible] አስተማረ አለ ። አንድም ነው እይጣላም ቢሉ አይከለም ነገር እንደ ማቴዎስ ሳይ [illegible] [illegible] እንዲህ ማለቱ ቢጠይቁት [illegible] [illegible] ያን ሲያይ ነው እንጂ ።

፪ ወይቤሎሙ ሶበ ትጼልዩ [illegible] ማቴዎስ ፮ ።
፪ ስትጸልዩም እንዲህ በሉ [illegible]
አቡነ ዘበሰማያት ።
በሰማይ ያለህ አባታችን [illegible]
ይትቀደስ ስምከ ።
ስምህ [illegible]
ትምጻእ [illegible]
[illegible]
ወይኩን ፈቃድከ ።
ፈቃድህ ይሁን ።
በከመ በሰማይ ።
በሰማይ እንደሆነች ።
ከማሁ በምድር ።
በምድር እንዲሁ ።

፫ ሲሳየነ ዘለለዕለትነ ሀበነ ዮም ።
፫ የለት ምግባችንን ስጠን ዛሬ ።

[illegible]
፬ [illegible] በደላችንን
[illegible] አቤቱ ።
[illegible] ቅቡረ [illegible]
[illegible]
[illegible]
አላ አድኅነነ ።
አድነን እንጂ ።
ወባልሐነ እምዘኩሉ እኩይ ።
ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ ።

፭ ወይቤሎሙ በምሳሌ እመበ እምኔክሙ ዘቦ አርክ ።
[illegible]
[illegible]
[illegible]

፭ ከናንተ ወገን ወዳጅ ያለው ሰው ቢኖር ።
ወሖረ ኀቤሁ መንፈቀ ሌሊት ወይቤሎ አርክየ ለቅሐኒ ሠለስተ ኅብስተ ።
በተሎ ሌሊት ወደሱ ሂዶ ወዳጄ ሆይ ሦስት እንጀራ አበድረኝ ቢለው ።
[illegible]
[illegible]
[illegible]

፯ ወይስጥዎ ዝኩ ዓርኩ እምውስጥ ።
[illegible] ይመልስለታል ።
ወይቤሎ [illegible] ።
አትዘብዝበኝ ።
ወዳእኩ ቀተርኩ ኆኅትየ ።
ደጄን ዘግቼ ተኝቻለሁ ።
ወደቂቅየ ይሰክቡ ምስሌየ ውስተ ብዕራት ወኢይክል ተንሥአ እህብከ ።
ተነሥቼም እንዳልሰጥህ ልጆች አልብሼ ተኝቻለሁ ቢለው ።

፰ እብለክሙ [illegible]
፰ ለጊዜው ተነሥቶ ባይሰጠው ።
እስመ አርኩ ውእቱ ።
ወዳጁ ነውና ።
ከመ ኢያንጥዮ ።
[illegible]
ይትኃሣእ [illegible] ፈቃዶ ። [illegible]
ተነሥቶ የወደደውን ያህል ይሰጠዋል ብዬ እነግራችኋለሁ [illegible] ። አንድም ይህም ምን ይጠቅመዋል ብሎ አምስት ስድስት ይሰጠዋል ። አንድም [illegible] [illegible] ። ከናንተ ወገን [illegible] ያለው ተነሣሒ ቢኖር ። ወሖረ ኀቤሁ ። [illegible] ከባቴ

ወደ እግዚአብሔር እመልሰዋለሁ ሦስት ዓመት ሦስት ወር ሦስት ቀን ሦስት ሰዓት ዕድሜ አሰጠኝ ። እስመ በጽሒኒ ማኅፈርየ ፤ ሞት ተፈርዶብኛልና ቢለው ። ሐተታ ማኅፈር አለው እግዚአብሔርስ ኢገብረ ሞተ አላ ረሲዓን ሰብእ ጸውዕዎ በቃሎሙ ወእርከ አምሰልዎ እንዲል አምሐቅል አለ፥ ሞት የባሕርይ እንዳይደለ ለማጠየቅ ።
ወአልብየ ዘአሰብጦ ።
ሞትን የማስቀርበት ሃይማኖት ምግባር የለኝምና ቢለው ።
ወይሠጦ ዝኩ ዓርኩ እምውስተ ።
ጌታም በመምህረ ንስሐ አድሮ ምሕረት ተከልክ ሏል ቢለው ። ወደቂቅየኒ ።
መላእክትም እንዳያማልዱ ምሕረት ተከልክሏል ቢለው ። ንጽሐሙ ለሕፃናት በሥጋሆሙ ወነፍሶሙኒ ዘእንበለ ሕማም እንዲል ፤ በንጽሕና ይመስ ሏቸዋልና ሕፃናት አላቸው ።
እብለክሙ ። ለጊዜው ባያደርግለት ተላጽቆተ ስኢል ያስደርግለታል ብየ እነግራችኋለሁ ። ሐተታ ሦስትም የተባሉ ፤ ጥምቀት ፤ ሥጋው ደሙ ። ንስሐ ናቸው ። ጥምቀት የአብ ፤ ሥጋው ደሙ የወልድ ንስሐም የመንፈስ ቅዱስ ። ንስሐስ ድካም ያለ በት ነው ለመንፈስ ቅዱስ አይስማማውም ብሎ ንስሐ የወልድ ሥጋው ደሙ የመንፈስ ቅዱስ ፤ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ፤ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት የሚሆን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ነውና ።

፱ ወአነሂ እብለክሙ ሰአሉ ወይትወሀበክሙ ማቴ. ፯፥፯ ማር. ፲፩፥፳፬ ዮሐ. ፲፬፥፲፫ ያዕ. ፩፥፭

፱ እኔም እላችኋለሁ ለምኑ ይሰጣችኋል ።
ጐድጕዱ ወይትረኃወክሙ ።
ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል ።
ኅሡ ወትረክቡ ።
እሹ ታገኙማላችሁ ።

፲ እስመ ኵሉ ዘሰአለ ይነሥእ ።

፲ የለመነ ሁሉ ያገኛል ።
ወዘሂ ኀሠሠ ይረክብ ።
የሻም ያገኛልና ።
ወለዘሂ ጐድጐደ ይትረኃዎ ።
ደጅ ለመታም ይከፈትለታል ።

፲፩ ወአመቦ እምውስቴትክሙ ዘሰአሎ ወልዱ ኅብስተ እቡነ ይሁቦ ። ማቴ፡ ፯፥፱ ።

፲፩ ከእናንተ ወገን ልጁ አባቱን ዳቦ ቢለም ነው ደንጊያ ይሰጠዋልን ።

፲፪ ወእመኒ ዓሣ ሰአሎ አርዌ ምድር ኑ ይሁቦ ህየንተ ዓሣ ።

፲፪ ዓሣ ቢለምነው ስለ ዓሣው እባብ ይሰጠዋልን ።
ወእመኒ እንቍቅሀ ሰአሎ አትራብን ይሁቦ ሀየን ቴሁ ።
እንቍላልስ ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን ።

፲፫ ወሶበ አንትሙ እንዘ እኩያን አንትሙ ተአምሩ ሠናየ ሀብተ ውኂበ ለውሉድክሙ ።

፲፫ እናንተ ስንኳ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን የምትወዱ ከሆነ እፎ ፈድፋደ አቡክሙ ዘበሰማያት ይሁብ ሠናየ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ለእለ ይስእልዎ ።
በሰማይ ያለ አባታችሁ ለሚለምኑት የመንፈስ ቅዱስን ሀብት እንዴት አብዝቶ ይሰጣቸው ።

በእንተ ጽሙም ጋኔን ዘአንጎ ።

፲፬ ወሀሎ ሀየ ያወፅእ ጋኔነ በሐመ ወጽ ሙመ ። ማቴ፡፱፥፴፪ ።

፲፬ ድዳ ደንቆሮ ጋኔንም ያወጣ ነበር ።
ወሶቤሃ ዝኩ ጋኔን ነበበ ወሰምዓ ውእቱ ጽሙም ።
ወበሐም ጋኔኑ በወጣ ጊዜ ድዳ ደንቆሮ የነበረው ተናገረ ።
ወአንከርዎ ሰብእ ።
ሰዎችም አደነቁት ።

፲፭ ወቦ እምውስቴቶሙ እለ ይቤሉ በብዔል ዜቡል በመልአኮሙ ለአጋንንት ያወፅኦሙ ለአ ጋንንት ማቴ፡ ፱፥፴፬ ማር፡ ፫፥፳፪ ።

፲፭ ከነሱ ወገን በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል አጋንንትን ያወጣል ያሉም አሉ ።

፲፰ ወአውሥአ ወይቤ እፎ ይክል ሰይጣን ለሰይጣን አውፅኦቶ ።

፲፰ ሰይጣን ሰይጣንን ማውጣት እንደምን ይቻለዋል ብሎ መለሰላቸው ።

በእንተ መናፍስት እኩያን ።

ወቦ እለ ያሜክርዎ ። የሚፈትኑት
ወየኀሥሡ ትእምርተ እምሰማይ ኀቤሁ ።
ከሰማይም ምልክት ያሳያቸው ዘንድ ይሹም ነበር ።

፲፯ ወውእቱሰ አእመሮሙ ዘይሄልዩ ፤
፲፯ እሱ ግን አሳባቸውን ዐወቀባቸው ፤
ወይቤሎሙ ኵላ መንግሥት እንተ ትትናፈቅ በበይናቲሃ ትማስን ።
እርስ በርሷ የምትለያይ መንግሥት ሁሉ ትጠፋለች፤
ወቤትኒ ላዕለ ቤት እመ ተናፈቀ ይወድቅ ውእቱ ቤት ።
ቤትም በቤት ላይ ይወድቃል ።

፲፰ ወእመሰ ሰይጣን ተናፈቀ በበይናቲሁ እፎ ይቀውም መንግሥቱ ።

፲፰ ሰይጣንስ እርስ በርሱ ከተለያየ እንዴት ይጸናል ግዛቱ ።
እስመ ትብሉ በብዔል ዜቡል በመልአኮሙ ለአጋንንት ያወፅኦሙ ለአጋንንት ።
በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል አጋንንትን ያወጣል ትላላችሁና ።

፲፱ ወእመሰ አነ በብዔል ዜቡል አወፅኦሙ ለአጋንንት ደቂቅክሙ በምንትኑ ያወፅእዎሙ ።

፲፱ እኔማ ሰይጣናትን በብዔል ዜቡል የማወጣ ከሆነ ልጆቻችሁ በምን ያወጧቸዋል ።
ወበእንተ ዝንቱ ይዛለፉክሙ ።
ስለዚህ እርሳቸው ይፈርዱባችኋል ።

፳ ወእመሰ አነ በአፅባዕተ እግዚአብሔር አወፅኦሙ ለአጋንንት ።

፳ እኔ ግን አጋንንትን በእግዚአብሔር ጣቶች ማለት በእግዚአብሔር ሥልጣን የማወጣቸው ከሆነ።
ዮጊኬ በጽሐት እንከሰ ኀቤክሙ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
እንግዲህ ገና የእግዚአብሔር መንግሥት ወደናንተ ደረሰች። ሐተታ ማቴዎስ በመንፈስ እግዚአብሔር ይላል ሉቃስ በአፅባእተ እግዚአብሔር አለ እንደ ምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም የሁለት ቀን ትምህርት የልሳን መለያየት ። አንድም አጽባእትም መንፈስም ቢል አንድ ነው ሥልጣነ እግዚአብሔር ማለት ነው ታችኛው የአብ መካከለኛው የመንፈስ ቅዱስ ላይኛው የወልድ ምሳሌ ባዕድ ጽፍርን እንደ ተወሐደ ባዕድ ሥጋን ተዋሕዷልና ።

፳፩ ወአምጣነ የዓቅብ ኃያል ዓጸደ ርሱይ በንዋየ ሐቅል ይድኅን ኵሉ ጥሪቱ ።

፳፩ አርበኛ በጋሻ በጦር ተሰልፎ ቤቱን በሚጠብቅበት ጊዜ ገንዘቡ ሁሉ ደህና ይሆናል ።
ወእመሰ ይመጽእ ዘይሄይሎ ይመውኦ ወይሰልቦ ንዋየ ሐቅሉ ዘይትአመን ቦቱ ።

፳፪ ከርሱ የሚበረታ የመጣ እንደሆነ ግን እሸንፎ የሚታመንበትን ጋሻና ጦሩንይ ወስድበታል ።
ወይትካፈል በርበሮ ወምህርከሁ ።
ገንዘቡን ይካፈለዋል ።

፳፫ ዘኢሀሎ ምስሌየ ፅድወየ ውእቱ ።
፳፫ ከኔ ጋራ ያልሆነ እርሱ ባለጋራዬ ነው ።
ወዘኢይትጋባእ ምስሌየ ይዘርወኒ ።
ከኔም ጋራ አንድ የማይሆን እርሱ ይለየኛል ።
፳፬ ወሶበ ይወፅእ ጋኔን እኩይ የዓውድ በድወ ኀበ አልቦ ማይ ።

፳፬ ከቶ ሰይጣን ከሰው በወጣ ጊዜ ውኃ ወደ ሌለበት ምድረ በዳ ይዞራል ።
ወየኃሥሥ ምንባረ ወመካነ ኀበ የአርፍ ።
የሚያርፍበት ቦታ ይሻል ።
ወእምከመ ኢረከበ ይብል እገብእ ውስተ ቤትየ ኀበ ወፃእኩ እምኔሁ ።
ያላገኘ እንደሆነ ግን ወደቀደመ ቦታዬ ወደ ወጣሁበት እመለሳለሁ ይላል ።

፳፭ ወመጺኦ ይረክብ እንዘ ያስተራክብ ዕጹወ ወሥርግወ ወሡስቁረ ወምሩገ ።

፳፭ በመጣም ጊዜ ተጠርጎ አጊጦ ያገኘዋል ።

፳፮ ወእምዝ የሐውር ወያመጽእ ምስሌሁ ሰብዐተ አጋንንተ ካልዓነ እለ የአክዩ እምኔሁ ።

፳፮ ከዚህም በኋላ ከርሱ የሚከፉ ሰባት አጋንንት ያመጣል ።
ወይበውኡ ወየኃድሩ ውስቴቱ ።
ገብተውም ያድሩበታል ።
ወይብእሶ ደኃሪቱ ለውእቱ ብእሲ እምቀዳሚቱ ።
የዚያም ሰው ከፊተኛው የኋለኛው የከፋ ይሆናል ።

ዘከመ ብፁዕ ውእቱ ዘይሰምዕ ቃለ እግዚአብሔር።

፳፯ ወእምዝ እንዘ ይትናገር ከልሐት አሐቲ ብእሲት በማዕከለ ሰብእ ።

፳፯ ከዚህ በኋላ ይህን ሲናገር አንዲት ሴት በሕዝቡ መካከል ጮኸች ።
ወትቤሎ ብፅዕት ከርሥ እንተ ጾረተከ ።
አንተን የፀነሰች ማኅፀን የተመሰገነች ናት ።
ወአጥባት እለ ሐፀንከ ።
አንተንም ያጠቡ ጡቶች የተመሰገኑ ናቸው አለችው

፳፰ ወይቤላ ውእቱኒ ብፁዓንሰ እለ ይሰምዑ ቃለ እግዚአብሔር ወየዓቅቡ ።

፳፰ እርሱም የተመሰገኑስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁ ናቸው አላት ። ሐተታ ብፅዕት ከርሥ ብፀዓት አጥባት ማለቷ እመቤታችንን ማመስገኑዋ ነው ፤ እሱ ብፁዓንሰ ማለቱ እመቤታችንን መንቀፉ ነውን ቢሉ እንዳይነቅፋትስ ይእቲ ተዓቢ እምኪሩቤል በንጽሕ ይላታል ብሎ ይህች ሴት በተንኮል መጥታለች ብፁዕ ብለው ብፅዕት ይለኛል ብላ አንች ብፅዕት አይደለሽም ። ብፁዓንሰ ወንጌልን ሰምተው የሚጠብቁ ናቸው አላት ።

በእንተ ትእምርተ ዮናስ ።

፳፱ ወእንዘ ጉቡአን ብዙኃን ለፀአ ወይትሀወኩ አኃዘ ይቤሎሙ ዛቲ ትውልድ እኪት ትእምርተ ተኃሥሥ ። ማቴ፡ ፲፪፡ ፳፱ ።

፳፱ ብዙ ሰዎች ተሰብስበውላቸው ሳሉ እንዲህ የክፉ ትውልድ ምልክትን ይሻሉ ። ወትእምርትሰ ኢይትወሀባ ዘእንበለ ትእምርተ ዮናስ ነቢይ ።
ምልክት ግን ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር አይሰጣትም ።

፴ ወበከመ ዮናስ ኮነ ትእምርተ ለሰብአ ነነዌ ። ዮሐ. ፱፥ ፭ ።

፴ ዮናስ ለነነዌ ሰዎች ምልክት እንደሆናቸው ያው ለዛቲ ትውልድ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስም ለዚች ትውልድ እንዲሁ ምልክት ይሆናታል ።

፴፩ ንግሥተ ዓዜብ ትትነሣእ እመ ደይን ምስለ ዛቲ ትውልድ ወትትዋቀሣ ። ፴፩ የዓዜብ ንግሥት በፍርድ ጊዜ ተነሥታ ከዚች ትውልድ ጋራ ትፋረዳለች ። እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር ትስማዕ ጥበቦ ለሰሎሞን ። የሰሎሞንን ጥበቡን ትሰማ ዘንድ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና ።
ወናሁ ዘየዓቢ እምሰሎሞን ሀሎ ዝየ ።
ከሰሎሞን የሚበልጥ እነሆ ከዚህ አለ ።

፴፪ ሰብአ ነነዌ ይትነሥኡ አመ ደይን ምስለ ዛቲ ትውልድ ወይትኳነንዋ ወይኬንንዋ ። ዮሐ. ፫፥፭ ።

፴፪ የነነዌ ሰዎች በፍርድ ጊዜ ተነሥተው ይከራከሩቃታል ። እስመ ነስሑ አመ ሰበከ ዮናስ ። ዮናስ ባስተማራቸው ጊዜ ንስሐ ገብተዋልና ።
ወናሁ ዘየዓቢ እምዮናስ ሀሎ ዝየ ።
ከዮናስ የሚበልጥ እነሆ ከዚህ አለ ።

፴፫ ወአልቦ ዘያኀቱ ማኅቶተ ከመ ያንብራ ታሕተ ምንባብ ወኢመ አኮ ታሕተ ከፈር ማቴ፭፥፲፭ ። ማር. ፬፥፳፩ ።

፴፫ መብራት አብርቶ ከዕንቅብ በታች ሰውሮ የሚያኖር የለም ።
ዘእንበለ ዲበ ተቅዋም ።
ከመቅረዝ ላይ ያኖሩታል እንጂ ።
ከመ ይርአዩ ብርሃኖ እለ ያንሶሰዉ ።
የሚመላለሱት ብርሃን ያዩ ዘንድ ።

፴፬ ማኅቶቱ ለሥጋከ ዓይንከ ውእቱ ። ማቴ ፮ ፡ ፳፪ ። ማር. ፬፥፳፩ ።

፴፬ ወእምጣነ ዓይንከ ብሩህ ውእቱ ኩሉ ሥጋከ ብሩህ ውእቱ ።
ዓይንህ የጸራ ያህል ሥጋህ ሁሉ የበራ ይሆናል ። ወእመሰ ዓይንከ ሕማሚ ወኩሉ ሥጋከ ጽልመት ውእቱ ።
ዓይንህ የሚታመም ከሆነ ግን እንደዚያ ሥጋህ ሁሉ ጨለማ ይሆናል ።

፴፭ ዑቅ እንከ ብርሃንከ ጽልመተ ኢይከውን ።
፴፭ ብርሃንህ ጨለማ እንዳይሆን እንግዲህ ተጠበቅ ።

፴፮ ወእምከመሰ ኩሉ ነፍስትከ ብሩህ ውእቱ ...

፴፮ ሰውነትህ ሁሉ የጸራ እንደሆነ ግን ምንም ጨለማ የሌለበት ... ወትከውን ... ሁለንተናህ የበራ ይሆናል ... ከመ ማኅቶት ... እንደ ፀሐይ ብርሃን ሲል ነው ።

በእንተ ኢየሱስ ወፈሪሳውያን ።

፴፯ ... ይብሎ አሐዱ ፈሪሳዊ ...

፴፯ ይህን ሲነግራቸው አንድ ፈሪሳዊ ከቤቱ ገብተህ ብላልኝ አለው ።
ወቦአ ወረፈቀ ። ገብቶም ተቀመጠ ።

፴፰ ወርእዮ ፈሪሳዊ አንከረ ...
፴፰ ፈሪሳዊውም አይቶ አደነቀ ... እስመ ... የቤተ ... አልታጠበምና ። አንድም በመብላቱ ጊዜ እጁን አልታጠበምና ።

፴፱ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አንትሙሰ ፈሪሳውያን ይእዜ እንተ አፍአሁ ተሐፅቡ ወታነጽሕዎ ለጽዋዕ ወለጻሕል ወለዝኒ ንዋይ ። ማቴ ፳፫፥ ፳፭ ።

፴፱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እናንተ ፈሪሳውያን ግን ጽዋውን ውጭውን ታጥባላችሁ ታነጹታላችሁም ።
ወእንተ ውስጡሰ ምሉእ ሐይደ ወአከየ ።
በውስጥ ግን ቅሚያና ክፋትን የተመላ ነው አላችሁ ።

፵ አብዳን አኮኑ ዘፈጠረ እንተ አፍአ ዘእንተ ውስጥኒ ፈጠረ ።

፵ እናንተ ሀላዋቶች የውጭውን የፈጠረ የውስጡንስ ፈጣሪ የለምን ።

፵፩ ወባሕቱ ዘይትረፈቀድ ሀቡ ምጽዋተ ።
፵፩ ነገር ግን የሚወድድ ነገር ምጽዋት ስጡ ።
ወኩሉ ንጹሕ ይከውንክሙ ።
ሁሉ ንጹሕ ይሆንላችኋል ።

፵፪ አሌ ለክሙ ጸሕፍት ወፈሪሳውያን እለ ታበውኡ ዐሥራተ እጸዉ ለአዛብ ወለጼናታም ወለኵሉ ኢሕማላት ወትትዔወርዎ ለፍትሐ እግዚአብሔር ወለፍቅረ እግዚአብሔር ።

፵፪ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ፍርድ ቸል ብላችሁ የጤናዳምንና የንስላልን የሚለቀመውንም ሁሉ ካሥር አንድ የምታወጡ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ወዮላችሁ ።
ወዘንተኒ ርቱዕ ትግበሩ ።
ይህንም ልታደርጉ ይገባል ።
ወዝክተኒ ኢትኅድጉ ።
ያንም አትተው ።

፵፫ አሌለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን ። ማቴ. ፳፫፡፯ ማር ፲፪፡፴፱ ሉቃ. ፳ ፵፮ ።

፵፫ ግብዞች ጸሐፍት ፈሪሳውያን ወዮላችሁ ፡
እስመ ታፈቅሩ ነቢረ ፍጽም በውስተ አዕዋዳት ።
በሸንጎ በላይ መቀመጥ ትወዳላችሁና ።
ወተአምኆ በውስተ ምሥያጥ ወርእሰ ምርፋቃት በውስተ ምሳሐት ።
በምሳ በላይ መቀመጥን በገበያ እጅ ሊነሷችሁ ።

፵፬ አሌ ለከሙ ጸሐፍት ፈሪሳውያን መደልዋን ።

፵፬ ግብዞች ጸሐፍት ፈሪሳውያን ወዮላችሁ ።
እስመ አንትሙ ከመ መቃብር ዘኢይትዓወቅ ዘያንሶሱ ሰብእ ላዕሌሁ ወኢየአምሮ ።
የሚመላለስበት ሰው እንዲያውቀው እንደተሰወረ መቃብር ናቸው ።

፵፭ ወአውሥአ አሐዱ እምጸሐፍተ ሀገር ።
፵፭ ካገር ጸሐፎችም አንዱ መለሰ ።
ወይቤሎ ሊቅ ዘንተ እንዘ ትብል ኪያነሁ ትጼዕል ።
መምህር ሆይ እንዲህ ማለትህ እኛን መንቀፍ ነው አለው ።

፵፮ ወይቤሎ ለከሙሂ ወለጸሐፍት ሀገር አሌ ለከሙ ። ማቴ ፳፫፡፬ ።

፵፮ ለናንተም ለጸፎችም ወዮላችሁ አለው ።
እስመ ታጸውርዎ ለሰብእ ጾረ ክቡደ ።
ሰውን ጽኑ ሸክም ታሸክሙታላችሁና ።
ወለሊከሙሰ ኢትለክፍዎ ወኢትገሥሥዎ በአሐቲ አፅባዕትክሙ ጥቀ ለውእቱ ጾር ።
እናንተ ግን ያን ሸክም ባንድ ጣታችሁ ስንኳ አትነኩትም ።

፵፯ አሌ ለከሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን እስመ ተሐንጹ መቃብሪሆሙ ለነቢያት እለ አበዊከሙ ቀተልዎሙ ።

፵፯ አባቶቻችሁ የገደሏቸውን የነቢያት መቃብር ታንጻላችሁና ወዮላችሁ ።

፵፰ አደመክሙኑ ምግባሮሙ ለአበዊክሙ ፤
፵፰ ያባቶቻችሁ ሥራ ደስ ይላችኋልን ።
ወስሊከሙ ሰማዕቶሙ ።
እናንተም ምስክሮች ናችሁ ።
እስመ ዘእሙንቱ ቀተሉ ወአንትሙ ተሐንጹ መቃብሪሆሙ ።
እርሳቸው የገደሏቸውን እናንተ መቃብራቸውን ትሠራላችሁና ።

፵፱ ወበእንተ ዝንቱ ትቤ ጥበቢሁ ለእግዚአብሔር ናሁ አነ እፌኑ ኀቤሆሙ ነቢያተ ወሐርያተ ።

፵፱ ስለዚህ የእግዚአብሔር ጥበብ ወልድ ነቢያትን ሐዋርያትን ወደርሳቸው እልካለሁ አለች ።
ወይቀትሉ እምኔሆሙ ከርሳቸውም ይገለላሉ ።
ወይሰድዱ ።
ካገርም አስወጥተው ይሰዷቸዋል አለች ።

፶ ከመ ይትበቀሎሙ በእንተ ደመ ኵሉ ነቢያት ዘተከዕወ እምፍጥረተ ዓለም እስከ ዛቲ ትውልድ

፶ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከዚች ትውልድ ድረስ በፈሰሰ በነቢያት ደም ሁሉ ይበቀላቸው ዘንድ ።

፶፩ እምደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ዘቀተልዎ በማእከለ ቤተ መቅደስ ወምሥዋዑ ለእግዚአብሔር ።

፶፩ ከአቤል ደም ጀምሮ ከቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደሉት እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ ።
እወ እብለከሙ ይትኃሠሥዋ ወይትቤቀልዋ ለዛቲ ትውልድ ።
ከዚች ትውልድ እንዲፈላለጉ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፶፪ አሌ ለከሙ ጸሐፍተ ሀገር ወፈሪሳውያን ።
፶፪ ያገር ጸሐፊዎችና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ ።
እስመ ነሣእክሙ መራሑተ ጽድቅ ወአእምሮ ወተኃብኡ ።
የውቀትና የውነት መክፈቻ መስዳችሁ ትሰውራላችሁና ማለት የተነገረውን ትንቢትና የተቈጠረውን ሱባኤ ዐውቃችሁ ሰውራችኋልና ።
ለሊከሙኒ ኢትበውኡ ።
እናንተም አትገቡ ።
ወልእለሂ ይበውኡ ትከልእዎሙ በዊአ ።
የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክሏቸዋላችሁ ።

፶፫ ወእንዘ ይነግሮሙ ዘንተ በቅድመ ኵሉ ሕዝብ አኃዙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ያመንዝዝዎ በእክይ ።

፶፫ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ይህን ሲነግራቸው ጸሐፍት ፈሪሳውያን አጽንተው ይጣሉት ጀመር ።
ወይትቄየምዎ ።
ቂም ያዙበት ።

፶፬ ወይንዕውዎ ።
፶፬ በነገር አደኑት ።
ወያስሕትዎ በቃለ አፉሁ ።
እናግረን እናስተዋለን አሉ ።

በእንተ ብኑእ ዘፈሪሳውያን

ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ ወተጋብአ ኅቤሁ አእላፍ ሰብእ ማቴ፡፲፮፡፮ ማር፡፰፡፲፭ ።

፩ ብዙ ሰዎች ወደሱ ተሰበሰቡ ።
እስከ ይትካየዱ በበይናቲሆሙ ።
እስኪጠቃጠቁ ማለት አንዱ አንዱን እስኪ ጠቀጥቀው ድረስ ።
ወአኃዘ ይበሎሙ ለአርዳኢሁ ቅድሙ ወተዓቀቡ እምነ ብሑአሙ ለፈሪሳውያን ።
ለደቀ መዛሙርቱ አስቀድሞ ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ ይላቸው ጀመረ ።
ዘውእቱ አድልዎ ።
እርሱም ግብዝነት ።

፪ እስመ አልቦ ክዱን ዘኢይትከሠት ።
፪ የማይገለጥ የተሸሸገ የለምና ።
ወአልቦ ኅቡእ ዘኢያስተርኢ ።
የማይታይ የተሰወረም የለም ።

፫ ወዘተናገሩ በጽልመት ይትናገርዎ በብርሃን ወይሰማዕ ።

፫ በጨለማ የተናገሩትን በብርሃን ይናገሩታል ይሰማል ።
ወዘኒ አልኆሰሱ በእዝን ይሰብክዎ በአጽራሕ ወበአንሕስት ።
በጆሮ የነገርዋቸውን በሰገነት ያስተምሩታል ።

፬ እብለክሙ ለክሙ ለአእርክትየ ኢትፍርሕዎሙ ለእለ ይቀትሉክሙ ሥጋክሙ ወነፍስትክሙ

፬ ለናንተ ለወዳጆቼ ሰውነታችሁን የሚገኗችሁን አትፍሩ እላችኋለሁ ።
ወእምዝ አልቦ ፈድፋደ ዘይክሉ ገቢረ ፤
ከዚህ በኋላ ከዚህ የበለጠ የሚበልጥ የሚሠሩት የለምና ።

፭ ወባሕቱ አርእየክሙ ዘትፈርሁ ።
፭ የምትፈሩትንስ አሳያችኋለሁ ።
ፍርህዎስ ለዘእምድኅረ ቀተለ ብውህ ሎቱ ከመ ይደይ ነፍሰኒ ወሥጋኒ ውስተ ገሃነም ።
መፍራትስ ከገደለ በኋላ ነፍስንና ሥጋን ወደ ገሃነም ያገባ ዘንድ ሥልጣን ያለውን እርሱን ፍሩት እንጂ ።
እወ እብለክሙ ኪያሁ ፍርሁ ።
እሱን ፍሩት ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፮ አኮኑ ኃምስ አዕዋፍ ይሰየጣ በክልኤ ጸሪቀ አሶርዮን ።

፮ አምስቱ ዎፎች በሁለት ናስ ይሸጡ የለምን።
ወአሐቲ እምኔሆን ኢትትረሳእ በቅድመ እግዚአብሔር ።
ከርሳቸው አንዲቱ በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም።
ሐተታ ማቴዎስ ሁለት ይላል ሉቃስ አምስት አለ አይጣሳም ቢሉ አይጣላም ማቴዎስ የውዱን ሉቃስ የረኪሱን ተናገሩ ። ሲወደድ አንድ ሳንድ ሲረክስ ባንድ ሁለት ባንድ ሦስት ይገዛልና ። አምስቱ አዕዋፍ ፡ ነቢያት ካህናት ደቂቀ እስራኤል ነገሥት ጻድቃን ሊቃውንት እለ ፈጸሙ ሕግ ናቸው።

፯ ወለክሙኒ ሥእርተ ርእስክሙኒ ኍሉ ኍሉቅ ውእቱ ።

፯ የእናንተስ የራስ ጸጉራችሁ ስንኳ የተቈጠረ ነው ።
ኢትፍርሁ እንከ ።
እንግዲህ አትፍሩ ።
እስመ እምብዙኃ አዕዋፍ ትኄይሱ አንትሙ ።
ከብዙ ዎፎች እናንተ ትሻላላችሁና ።

፰ እብለክሙ ኵሉ ዘየአምን ብየ በቅድመ ዕጓለ እመሕያው አነኒ አአምኖ በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር ። ማቴ ፲፡ ፴፪ ማር. ፰፡ ፴፰ ።

፰ በሰው ፊት ያመነብኝን ሁሉ በእግዚአብሔር መላእክቶች ፊት አምነዋለሁ ።

፱ ወለዘሰ ክህደኒ በቅድመ ሰብእ አነኒ እክህዶ በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር ፪. ጢሞ. ፪፡ ፲፪ ።

፱ በሰው ፊት የካደኝን እኔም በእግዚአብሔር መላእክቶች ፊት እክደዋለሁ ።

፲ ወኵሉ ዘነበበ ቃለ ጽርፈት ላዕለ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ይትኃደግ ሎቱ ። ማቴ. ፲፪፡ ፴፩፡ ማር. ፫፤ ፳፰ ።

፲ በሰው ልጅ ላይ የስድብ ነገር የሚናገር ሁሉ ኃጢአቱ ይሰረይለታል።
ወዘሰ ነበበ ቃለ ጽርፈት ላዕለ መንፈስ ቅዱስ ኢይትኃደግ ሎቱ

በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ነገር የሚናገር ግን ኃጢአቱ አይሰረይለትም ።
ኢበዝ ዓለም ።
በዚህም ዓለም ።
ወኢበዘይመጽእ ዓለም ።
በሚመጣውም ዓለም ሁኖ ።

፲፩ ወሶበሂ ይወስዱክሙ አዕዋዳተ ።

፲፩ ወደዐደባባይ በወሰዷችሁም ጊዜ ።
ወኀበሂ መላእክት ።
ወዳለቆችም ።
ወነገሥት ወመኳንንት ።
ወደ መኳንንትና ወደ ነገሥታት በወሰዷችሁ ጊዜ።
ኢትሐልዩ ዘከመ ትብሉ ወዘከመ ትትናገሩ ።
የምትናገሩትን የምትመልሱትን አታስቡ ።

፲፪ እስመ መንፈስ አቡክሙ ውእቱ ይትናገር ላዕሌክሙ ሶቤሃ ።

፲፪ ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በናንተ አድሮ ይናገራል ።

በእንተ ትዝኅርት ወበእንተ እኩይ ባዕል ።

፲፫ ወይቤሎ አሐዱ እምሕዝብ ሊቅ በሎ ለእኁየ ይክፍለኒ ርስትየ ።

፲፫ ከሕዝቡ አንዱ መምህር ሆይ ርስቱን እንዲያካፍለኝ ወንድሜን እዘዝልኝ አለው ።

፲፬ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አንተ ብእሲ መኑ ሤመኒ ከፋሌ ወመኰንነ ላዕሌክሙ ።

፲፬ አንተ ሰው በናንተ ላይ ገዢ ዳኛ አድርጎ ማን ሾመኝ አለው ። ሐተታ እጅምር ከመ ልዑል ይኲንን መንግሥተ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ወለዘ ፈቀደ ይሁብ ይል የለም ቢሉ አልመጣሁ ብትም ሲል እንዲህ አለ ። አንድም ይህ ሰው በተንኰል ተነሥቷል እንዲህ ያልኩት እንደሆነ እሱማ እኔን ተከትሎ ይሄዳል ገንዘቡ ላንተ ይሁን ይለኛል ብሎ በተንኰል መጥቷልና የሕሊናውን ዐውቆበት እንዲህ አለ ።

፲፭ ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ዑቁ ወተዓቀቡ እምነ ኵሉ ትዕግልት ።

፲፭ ይህ ሰው እንዲህ ማለቱ ገንዘብ ወዶ ወንድሙን ጠልቶ እንጂ ነው ከፍቅረ ንዋይ ተከልከሉ አላቸው ።
እስመ አኮ በአብዝኆ ንዋይ ዘየሐዩ ሰብእ ።
ሰው የሚድን በገንዘብ ብዛት አይደለምና ።

፲፮ ወመሰለ ሎሙ ወይቤሎሙ አሐዱ ብእሲ ባዕል ዘሠምረ ሎቱ ተግባሩ ።

፲፮ ቢያሳርስ ቢያስነግድ የበጀለት ወይለዎ ብሔር ።
አገር የተቀበለው አንድ ባለጠጋ ሰው ነበር ብሎ መስሎ ነገራቸው ።
ወሀለየ በልቡ በልቡ አሰበ

፲፯ ምንተ እሬሲ ዘአልብየ ኀበ እዘግብ እክልየ ወበረከትየ ።

፲፯ አዲሱን እህሉን የከረመውን የምሰበስ ብበት ጎታ የሌኝ ምን አደርጋለሁ አለ ።

፲፰ ወይቤ ከመዝ እገብር ።

፲፰ እንዲህ አደርጋለሁ አለ ።
እነሥት ዘትካት መዛግብትየ ።
የቀደመውን ጎተራዬን አፍርሼ ።
ወአሐንጽ ካልዓ ዘየዓቢ ።
ሌላ የበለጠ እሠራለሁ ።
ወእዘግብ ህየ እክልየ ወበረከትየ ።
የከረመውንም የዘንድሮውንም እሰበስባለሁ

፲፱ ወእብላ ለነፍስየ እ ነፍስየ ብኪ ብዙኀ በረከት ዘዘገብኪ ለኪ ዘየዓክለኪ ለብዙኀ ዓመታት። ሲራ ፲፩ ፤ ፲፱ ።

፲፱ ሰውነቴን ለብዙ ዘመን የሚበቃሽ የሰበ ሰብኩልሽ ብዙ ገንዘብ አለሽ ።
አዕርፊ እንከ ብልዒ ወስትዪ ወተፈሥሒ ።
እንግዲህ ወዲህ በልተሽ ጠጥተሽ ደስ ይበልሽ እላታለሁ ብሎ አሰበ ።

፳ ወይቤሎ እግዚአብሔር እ አብድ በዛቲ ሌሊት ይነሥእዋ ለነፍስከ ንምኔከ ።

፳ እግዚአብሔርም አለው አንተ ሰነፍ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከሥጋህ ይለዩዋታል ካንት ሊወ ስዷት ።
ለመኑ እንከ ይከውን ዝንቱ ዘአስተዳለውከ ።
ይህ ያሰናዳኸው ለማን ይሆናል አለው ።

፳፩ ከማሁኬ ዘይዘግብ ሎቱ መዝገበ ዘኢኮነ እምእግዚአብሔር ብዕሉ ።

፳፩ በእግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነ ገንዘብ እሰበስባለሁ የሚል ሰው ሁሉ እንደዚህ ሰው ነው አንድም ዘኢኮነ ብዕሉ እምእግዚአብሔር ይላል ፣ ብዕሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ያይደለ ሰው ሁሉ እንደዚህ ሰው ነው ።
ሐተታ ፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ ያይደለ ምን አለ ቢሉ ሰጥቶለት በልቶለት የበረከተ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። ሳይበላለት ሳይጠጣለት ሳይለብስለት ጦሙን እየዋለ ጥሬ እየበላ ለሰው ሳይሰጥለት የበረከተ እንደሆነ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ አይ ባልም በምሳው ከበረ ይባላል እንጂ ። አንድም

ወመሰለ ሎሙ ብሰሀ መልስ ፡ ልጅነት የተሰጠውንት የተቀበለችው አዳም ነበር ።

ወነሰየ ፡ የባሕርይ አምላክነት የለኝ ምን አደርጋለሁ ምን ለአድርግ አሰ ። ወይቤ ከመዝ እገብር ። ይህን የጸጋ አምላክነትን ትቼ የባሕርይ አምላክነትን ገንዘብ አደርጋለሁ ። ወእብላ ። ሰውነቴን ገንዘብ ያደረኩልሽ የባሕርይ አምላክነት አለልሽ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አሰ ።

ወይቤሎ እግዚአብሔር አንተ ሰነፍ ሰው በዚች ሌሊት ነፍስህን ከሥጋህ ይለዩዋታል ገንዘብ ያደረግኸው የባሕርይ አምላክነት ለማን ይሆናል አለው። ወእመ በላዕክሙ እምውእቱ ዕፅ ሞተ ትመውቱ ያለው ነገር ሊፈጸም ሽህ ዘመን ሊመላው ሰባ ዘመን ሲቀረው ሙቷልና ፡ ወእሕጸረ ሰብዓ ከራማተ እንዲል መላ ዘመኑን ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ነው ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ እንዱ ቀን አልተፈፈጸመም ። ከማሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ የይደለ ከብርን አከብራለሁ የሚል ሰው ሁሉ እንደ አዳም ነው ።

ዘኢኮነ ብዕሉ ከብሩ በእግዚአብሔር ፈቃድ ያይደለ ሰው ሁሉ እንደ አዳም ነው ።
ወሶበ ተናገረ ዘንተ ከልሐ ወይቤ ዘቦ እዕዛን ሰማዕያን ለይስማዕ ።
ይህን በተናገረ ጊዜ ዦሮ ያለው ይስማ አለ ።

ዘከመ ኢይደልዎ ለክርስቲያን ተዐፅቦት በከንቱ ።

፳፪ ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ በእንተ ዝንቱ እብለክሙ ኢትሃልዩ ለሥጋክሙ ዘትለብሱ ወለነስፍክሙ ዘትሰትዩ ። መዝ ፡ ፶፬ ፡ ፳፪ ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፭ ፡ ፩ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

፳፪ ለደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ ለሥጋችሁ የምትለብሱት ለነፍሳችሁ የምትበሉትን አታስቡ እላችኋለሁ አላቸው ።

፳፫ እስመ ነፍስ ተዓፅብ እምሲሲት ።

፳፫ ከመብል ነፍስ ትችገራለችና ፡
ወሥጋ የዓፅብ እምዓራዝ ።
ሥጋም ከልብስ ይቸገራልና ።

፳፬ ርእዩ ዕጕለ ቋዓት ዘኢይዘርዑ ወኢየዓርሩ ወአልቦሙ መዛግብት ።

፳፬ የማይዘሩ የማያጭዱ ማከማቻ የሌላቸው የቁሮች ጫጩቶችን ተመልከቱ ።
ወኢውማጥያት ።
ጎተራም የሌላቸውን ።
ወእግዚአብሔር ይሴስዮሙ ።
እግዚአብሔር ግን ይመግባቸዋል ። ሐተታ ማቴዎስ አዕዋፈ ሰማይ ይላል ሉቃስ ዕጕለ ቋዓት አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም የሁለት ቀን ትምርሀት የልሳን መለያየት ነው ። አንድም አዕዋፍ የወል ስማቸው ። ቋዓት የጕልማ ስማቸው ነው ። ማቴዎስ የወል ስማቸውን ሉቃስ የጉልማ ስማቸውን ተናገረ ። ዕጕል ማለቱ ግን በሚጸናባቸው ሲናገር ሲወለዱ ፍህም መስለው ይወለዳሉ እናት አባታቸው ደንግጠው ጥለዋቸው ይሄዳሉ ። ከአካላቸው ርጥበት አይታጣምና ተሐዋስያን ርጥበቱን ሲሹ ይቀርባሉ፡ እስከ አርባ ቀን ድረስ በትንፋሻቸው እየሳቡ ሲመገቡ ይሰነብታሉ ። ከአርባ ቀን በኋላ ጠጉር ያበቅላሉ በመልክ ይመስሏቸዋል ተመልሰው ይረዷቸዋልና በጸናው ተናገረ ።
እፎ እንከ ፈድፈደ ትኄይሱ አንትሙ እምአዕዋፍ።
እናንተማ ከወፎች እንደምን ትበልጡ ።

፳፭ መኑ እምኔክሙ በሐልዮ ዘይክል ወስኮ አሐደ እመተ በዲበ ቆሙ ።

፳፭ ከናንተ ወገን አስቦ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ ሙሉ ቁመት ማከል የሚቻለው ማነው ፡

፳፮ ወሶበ ኢትክሉ ዘንተ ዘይቀልል ለምንት ትሔልዩ ዘየአፅብ ።

፳፮ ይህን ትንሹን ማድረግ የማይቻላችሁ ከሆነ ለምን በሌላው ታስባላችሁ ።

፳፯ ናሁ ጽጌያተ ገዳም ርእዩ ዘከመ ይልሕቁ ኢይጸምው ወኢይፈትሉ ።

፳፯ ሳይደክሙ ሳይፈትሉ እንዴት እንዲያድጉ ጽጌያትን እዩ ።
እብለክሙ ከመ ሰሎሞን ጥቀ ኢለብሰ በኵሉ መዋዕለ ክብሩ ከመ አሐዱ እምእሉ ።
ሰሎሞን ስንኳ ክብሮበት ባለ ዘመን ሁሉ ካበቦች እንዳዱ አለበሰም ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፳፰ ወለእመ ከነ ሣርወ ጽጌ ዘዮም ሀሎ ወጌሰመ ይትወደይ ውስተ እሳት ዘከማሁ ይሬሲ እግዚአብሔር ።

፳፰ ነገ በእሳት የሚጣለውን ዛሬ በልምላሜ ያለውን ቅጠል እግዚአብሔር እንዲህ የሚያደርገው ከሆነ ።

፳፱ እፎ እንከ ፈድፋደ ለክሙ ሕጹጻነ ሃይማኖት ።

፳፱ እናንተ ሃይማኖት ያነሣችሁ ለእናንተ እንደ ምን ያድርግላችሁ ።
አንትሙሂ ኢትኅሥሡ ዘትበልዑ ወዘትሰትዩ ።
እናንተም የምትበሉትን የምትጠጡትን በሚያስጨንቅ አሳብ አትሹ ።
ወኢትትፋለሱ ።
ካንዱ ወዳንዱ አትበሉ ።

ወኢትጽሐቅዎ ። [illegible]

፴ እስመ ዘንተሰ ኵሎ አሕዛበ ዓለም ዘአፍአ የኃሥሥዎ ፤

፴ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይሹታልና ፤
ወለክሙሰ የአምር አቡክሙ ከመ ዘንተ ኵሎ ተኃሥሡ
ለናንተስ ይህን ሁሉ እንድትሹ አባታችሁ ያውቃል ፤

፴፩ ወባሕቱ ኅሡ መንግሥተ እግዚአብሔር ወጽድቆ ፤

፴፩ እናንተ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ፡ ወዝንቱሰ ኵሉ ይትዌሰከክሙ ይህስ ሁሉ ይጨመርላችኋል

፴፪ ኢትፍራህ እንእስ መርዔት ። አንተ ታናሽ መንጋ አትፍራ እእብ መርዓት ኤጲስ ቆጶስ ካህናት እንዲህማ ከሆነ ሕዝቡን ምን እመግባቸዋለሁ ብለህ አትፍራ ፡ እንታስተቶሰዋ ለነዓስ መርዔት ይላል አብነት ምእመናንን አታጽክሟቸው ።
እስመ ሠምረ አቡክሙ የሀብክሙ መንግሥቶ ።
ሰማያዊ አባታችሁ መንግሥተ ሰማያትን ሊሰጣችሁ ወዷልና

፴፫ [illegible] ቴዋል ቲያ ። [illegible]
[illegible]
የማያረጅ ከረጢት ለናንተ አድርጉ ።
[illegible] ዘበሰማያት ዘኢየኀልቅ ።
[illegible] ድልብም በሰማይ ነገብ ኢይረክቦ ሠራቂ [illegible]
[illegible]

፴፬ [illegible] ሀሎ መዝገብክሙ ህየ ይሄሉ ልብ ክሙ ።

፴፬ ግምዛችሁ ካለበት ልቡናችሁ ይኖራል ፤

በእንተ ተጊሆ ።

፴፭ ወይኩን ቅኑት ሐቌክሙ ወኅትወ ማኅቶትክሙ ።

፴፭ ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁ የበራ [illegible] ልቡናችሁ በዕውቀት የጸና እጽምሮዋችሁ ፤ የጸናም ይሁን ።

፴፮ ወአንትሙኒ ኩኑ ከመ እደው እለ ይጸንሑ እግዚኦሙ እስከ የአቱ እምከብካብ ።
[illegible] ከሠርግ እስኪመለስ [illegible] ጠብቁ ሰዎች ሁኑ ። ከመ ሶበ መጽአ ወጐድጐደ የርኅዉ ሎቱ ።
በመጣ ጊዜ ፈጥነው ይከፍቱለት ዘንድ እንድም በመጣ ጊዜ ለተዋሕዶ በቅድሚያ ትግሥ ዘንድ ጌታቸውን ደጅ እንደሚጠኑት ምእመናን ሁኑ ።

፴፯ ብፁዓን እሙንቱ አግብርት ሶበ ይመጽእ እግዚኦሙ እለ ይረክቦሙ እንዘ ክሙዘ ይትገብሩ ወይትግሁ ።

፴፯ ጌታቸው በመጣ ጊዜ ተግተው እንዲህ ሲያደርጉ የሚገኙ ባሮች የተመሰገኑ ናቸው ። እንድም ጌታ በመጣ ጊዜ ለተዋሕዶ በቅተው የተገኙ ምእመናን የተመሰገኑ ናቸው ። አማን እብለክሙ ከመ ይቀንት ሐቌሁ ወያረፍቆሙ ወያንሶሱ ማዕከሎሙ ወይትለአኮሙ ፤ ታጥቆ ያበላፋቸዋል ብየ እንዲያሳልፋቸው በውነት እነግራችኋለሁ ። እንድም ምስጋናውን ጀምሮ ይሰጣቸዋል ብየ እንዲሰጣቸው በውነት እነግራችኋለሁ በዚህም መጻሕፍት ተባብረውበታል ። ሔኖክ ኀሩ ይኒ ይቄድስ ብኃይል ሱቱኤል ዕዝራም አሜሃ ይፌጽም ቀላዬ መመሲሕየ ። ሐዋርያቱም ወአመ ኵሉ ገነየ ሎቱ ወልድኒ ይገኒ ለዘአግነየ ሎቱ ኵሎ ብኃል ። ሊቁም በቅዳሴ አሜሃ ደብተራ ብርሃን ይትከል ወመኃትወ ብርሃን ይሰፉሕ ወያቀውሞሙ ለካህናት በየማኑ ወለዲያቆናት በጸጋሙ ወያርኢ [illegible] ሊቀ ካህናትነቱ ጀምሮ ይሰጣቸዋልና ። ያን ጊዜስ ስንኳን ገኙ በሌሎችም የለባቸውም ብሎ በተገኘ ሥጋ ሰለታየ በዕለተ ዓርብ ባደረገው ትልእኮ ዋጋቸውን የሚሰጣቸው ስለሆነ እንዲህ አለ ።

፴፰ ወእመኒ በካልዕት ወእመኒ በሣልስት ሰዓተ ሌሊት ሶበ መጽአ ወረከቦሙ ከመዝ ብፁዓን እሙንቱ እልክቱ አግብርት ።

፴፰ በሁለተኛውም ሰዓት ቢሆን በሦስተኛውም ሰዓት ቢሆን በመጣ ጊዜ እንዲህ ቢያገኛቸው እኒያ ባሮች የተመሰገኑ ናቸው ።

፴፱ ወዘንተ ባሕቱ አእምሩ ። ማቴ ፳፬ ፡ ፵፫ ።
፴፱ ይህንንም ዕወቁ ።
ሶበሰ የአምር በዓለ ቤት እንተ ጊዜ ይመጽእ ሠራቂ እምተግሀ ወእምሀለወ ።
ባለቤት ሌባ የሚመጣበትን ሰዓት ዐውቆ ቢሆን ተግቶ በጠበቀ ነበር ።
ወእምኢኀደገ ይክረዩ ቤቶ ።
ቤቱንም ይምሱት ዘንድ ባልተወ ነበር ።

፵ ወአንትሙኒ ድልዋኒክሙ ሀልዉ ።
፵ እናንተም ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ።
እስመ ፡ በጊዜ ፡ ኢተሐዘብክሙ ፡ ይመጽእ ፡ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ባልጠረጠራችሁት ጊዜ ይመጣልና ።

፵፩ ወይቤሎ ጴጥሮስ እግዚኦ ለነኑ ትሜስል ዘንተ ምሳሌ ።

፵፩ ጴጥሮስም አቤቱ ይህን የምትመስል ለኛ ነውን ።
ወሚመ ለኵሉ ።
ወይስ ለሁሉ ነው አለው ።

፵፪ ወይቤሎ እግዚእነ ።
፵፪ ጌታም መለሰ ።
መኑ እንጋ ውእቱ መጋቢ ኄር ወምእመን መጠቢብ ዘይሰይሞ እግዚኡ ላዕለ ኵሉ ቤቱ ።
ጌታ በባሮቹ ላይ የሚሾመው የታመነ ብልህ አስተዋይ ሹም ማነው ።
ከመ የሀቦሙ ሲሳዮሙ በበጊዜሁ ።
ምግባቸውን በየጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ።

፵፫ ብፁዕ ውእቱ ገብር ዘመጺኦ እግዚኡ ይረክቦ እንዘ ከመዝ ይገብር ።

፵፫ ጌታው በመጣ ጊዜ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው የተመሰገነ ነው ።

፵፬ አማን እብለክሙ ከመ ላዕለ ኵሉ ንዋዩ ያሜግቦ ።

፵፬ በከብቱ ሁሉ ላይ ይሾመዋል ብየ በእውነት እነግራችኋለሁ ።

፵፭ ወእመሰ ይቤ ውእቱ ገብር እኩይ በልቡ ይጐነዲ እቲወ እግዚእየ ።

፵፭ ያ ክፉ ባርያ ግን በልቡ ጌታዬ የሚመለስበት ገና ነው ቢል ።
ወይእኅዝ ይዝብጥ ወያመንዝዝ ደቀ ወአዋልደ ዘቤተ እግዚኡ ይበልዕ ወይሰቲ ምስለ ሰካርያን ወይሰክር ከሰካሮች ጋራ እየበላ እየጠጣ እየሰከረ የጌታውን ወንዶች ባሮች ሴቶች ባሮች ሊመታ ይጀምራል ።

፵፮ ወይመጽእ እግዚኡ ለውእቱ ገብር በዕለት ኢትሕዘበ ወበጊዜ ኢያእመረ ።

፵፮ የዚያ ያባርያ ጌታው ባላወቀው ሰዓት ባልጠረጠረው ዕለት መጥቶ ።
ወይመትሮ እምዕከሉ ።
ይለየዋል ይሸረዋል ።
ወያገብእ ወይሬሲ መክፈልቶ ምስለ አለ ኢየአምኑ ።
ፋንታውንም ከማያምኑ ጋራ ያደርግበታል ።

፵፯ ዝኩሰ ገብር ዘየአምር ፈቃደ እግዚኡ ወኢ ይገብር ።
[illegible]
ወኢያስተዳሉ ዘከመ ይፈቅድ ።

እንደ ፈቃዱም የማያደርግ ባርያ ግን ብዙን መቅሠፍት ፤
ፍዳው ብዙ ነው ።

፵፰ ወዘሰ ኢየአምር ለእመ ኢገብረ ኀዳጠ መቅሠፍተ ።

፵፰ የጌታውን ፈቃድ የማያውቅ ግን ባይሠራ ፅዳው ጥቂት ነው ።
እስመ ለኵሉ ዘብዙኃ ወሀብዎ ብዙኃ ይትኃሠሥዎ ።
ብዙ ከሰጡት ሁሉ ብዙ ይሹበታልና ።
ወለዘሂ ኅዳጠ አማኅፀንዎ ኅዳጠ ይትኃሠሥዎ ።
ጥቂት ያስጠበቁትንም ጥቂት ይመረመሩታል ።

፵፱ እሳተ አምጻእኩ ላብሔር ።
፵፱ በሀገር እሳትን አመጣሁ ማለት ለሰው ሁሉ ሃይማኖትን አስተምራለሁ ።
ወምንተ እፈቅድ ዘእንበለ አንድዶታ ።
እሷን ከማንደድ በቀር ሌላ ምን እሻለሁ ሃይማኖት ልትነገር እሻለሁ እንጂ ሌላ ምን እሻለሁ ።

፶ ወባሕቱ ብየ ጥምቀት ዘእጠመቅ ።
፶ ነገር ግን የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ ማለት የምሞታት ሞት አለችኝ ።
ወጥቀ እትኤገሥ እስከ እፌጽማ ።

እስከሞት ድረስ ሃይማኖትን ከመግለጥ እከለከላለሁ ሐተታ ። ጌታ ካልሞተ ካሣ አይፈጸምም ካሣም ካልተፈጸመ ልጅነት አይሰጥም ልጅነትም ካልተሰጠ ሃይማኖት አይገለጥምና ። ምነው ሃይማኖት አይቀድምም ልጅነት አይከተልምን ቢሉ ወአልቦ ዘይክል ብሂለ እግዚእ ኢየሱስ ዘእንበለ ዘመንፈስ ቅዱስ ሳዕለሁ እንዲል መጸናቱን መግለጹን ሲያይ እንዲህ አለ እንጂ እውነት ነው ሃይማኖት ይቀድማል ልጅነት ይከተላል ። አንድም እሳተ አምጻእኩ ብለህ መልስ ለሰው ልጅነትን አመጣሁ ። ወምንተ እፈቅድ ልጅነት ልትሰጥ እወዳለሁ እንጂ ሌላ ምን እሻለሁ ወባሕቱ ነገር ግን የምሞተው ሞት አለኝ ወጥቀ እትኤገሥ እስከ ሞት ድረስ ልጅነትን ከመስጠት እከለከላለሁ አሁን የተመቸ ጌታ ካልሞተ ካሣ አይፈጸምም ካሣም ካልተፈጸመ ልጅነት አይሰጥምና ።

፶፩ ወይቤሎሙ ለሕዝብ ይመስለክሙኑ ሰላመ ዘአምጻእኩ ለምድር ።

፶፩ ለሕዝቡ ለምድር ሰላምን ያመጣሁ ይመስላችኋልን አላቸው ።

፶፪ አልቦ እብለክሙ ።
፶፪ አይደለም እላችኋለሁ ።
ዘእንበለ መጥባሕት ወፍልጣን መለያየትን ሰይፍን ነው እንጂ [illegible] ህለዉ ውስተ ፩ ቤት ይትፈለጡ [illegible] ።

ከዛሬ ጀምሮ አምስት ሰዎች ባንድ ቤት ቢኖሩ ሦስቱ ከሁለቱ ይለያሉ ።
ወይትፌለጡ ክልኤቱ እምሠለስቱ ።
ሁለቱም ከሦስቱ ይለያሉ ።
ወይትፌለጥ አሐዱ እምካልኡ ።
አንዱም ካንዱ ይለያል ።

፶፫ ወይትፌለጥ አብ እምወልዱ
፶፫ አባት ከልጁ ይለያል ።
ወወልድኒ እምአቡሁ
ልጅም ካባቱ ይለያል ።
ወትትፌለጥ እም እምወለታ ።
እናትም ከልጅዋ ትለያለች ።
ወወለትኒ እምእማ ።
ሴት ልጅም ከናትዋ ።
ወሐማትኒ እመርዓታ ።
አማትም ከምራቷ ።
ወመርዓትኒ እምሐማታ ።
ምራትም ካማቷ ። ሐተታ ኃምስቱ የተባሉ ሐሳዌ ኤልያስ ሐሳዌ ኤልሳዕ ሐሳዌ አብድዩ ሄኖክ ኤልያስ ናቸው ሦስቱ ከሁለቱ ይለያያሉ አለ በክህደት ሁለቱ ከሦስት ይለያያሉ አለ በሞት አንድም ኃምስቱ የተባሉ አራቱ ባሕርያተ ሥጋ አምስተኛ ባሕርየ ነፍስ ናቸው ሦስቱ ከሁለቱ ይለያሉ አለ ነፍስ ስት ለይ ንፋስ እሳት ይለያያሉ ሁለቱ [illegible] ይገኛሉና ። አንድም ኃምስቱ የተባሉ ኃጢአት ሰውነት ሰይጣን ነፍስ መንፈስ ቅዱስ ናቸው ። ሦስቱ ከሁለቱ ይለያሉ አለ ። ኃጢአት ሰውነት ሰይጣን ናቸው ሁለቱ ከሦስት አለ ነፍስ መንፈስ ቅዱስ ሁለቱም ይለያያሉ ማለት ጠላት ገል ጠጠር ይጥላል ባለቤት የነቃበት ውሻ የሚጮኽበት እንደ ሆነ ይመለሳል ። ባለቤት ያልነቃበት ውሻ ያልጮኸበት እንደሆነ ገብቶ ባለቤቱን ገድሎ ቤቱን ዘርፎ ይሄዳል ። ሰይጣንም በነፍስ ዋዊት ጽኑት ያገኘበት እንደሆነ ጥልቅ ብሎ ገብቶ ከሕይወቷ ከመንፈስ ቅዱስ ይለያታልና ወለእመ ረከበ ንቡተ ሙባአ ውእቱኒ ያርኅቦ ለመካን እንዲል ።

፶፬ ወእምዝ ይቤሎሙ ለሕዝብ ሶበ ትሬእዩ ደመና ዘይሰርቅ መንገለ ዓረብ ዝናም ለመጺእ ዘመዝ ይከውን ትብሉ ማቴ ፲፮ ፪ ።

፶፬ ለሕዝቡም ለመዝነምም በምዕራብ በኩል ደመና ያያችሁ እንደሆነ እንዲህ ይሆናል ትላላችሁ አላቸው ።

፶፭ ወሶበ ይነፍሕ ነፋስ ዓዜብ ሐሩር ለመጺእ ከመዝ ይከውን ትብሉ ።

፶፭ ትኩሳት ለማምጣት የዓዜብ ነፋስ የነፈሰ እንደሆነ እንዲህ ይሆናል ትላላችሁ ።

፶፮ ኦ መደልዋን ለገጸ ሰማይ ወምድር ተአምሩ ፈክሮቶ ።

፶፮ እናንተ ግብዞች የሰማይና የምድርን ፊት መመርመር እናውቃለን ትላላችሁ ።
ወእፎ ኢተአምሩ ኣመክሮቶ ለዝንቱ መዋዕል ።
ይህን ወራት እንደምን አታውቁ ።

፶፯ ወለምንትኑ ኢትፈትሑ ጽድቀ ለሊክሙ ወዘይደሉ ላዕለ ነፍሳቲክሙ ።

፶፯ እናንተ ራሳችሁ ምነው እውነት አትፈርዱ ።

በእንተ ዕርቅ ።

፶፰ ወሶበ ተሐውር ምስለ ዕድውከ ኀበ መልአክ ተዓረቅ በፍኖት ። ማቴ ፭ ፳፭ ።

፶፰ ከባለጋራህ ጋራ ወደዳኛ በምትሔድበት ጊዜም ከባለጋራህ ጋራ በመንገድ ታረቅ ።
ወሰልጥ ዘትፈድዮ ።
የምትከፍለውንም ጨርሰህ ስጥ ።
ከመ ኢይትባጽሐከ ኀበ መኰንን ።
ወደ ዳኛ እንዳያደርስህ ።
ወመኰንን ይሚጥወከ ለወዓሊሁ ።
ዳኛውም ለሎሌው ይሰጥሃል ።
ወወዓሊሁ ይሞቅሐከ ።
ብላቴናውም ያስርሃል ።

፶፱ እብለከ ከመ ኢትወፅእ እምህየ እስከ ሶበ ትሜልጥ ደኃሪተ ገመስ ዘላዕሌከ ።

፶፱ የኋለኛውንም ድጥኙ እስክትሰጥ ድረስ ከዚያ አትወጣም ብየ እነግርሃለሁ ።

ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ገቢረ ንስሐ በሁሮህ ።

ምዕራፍ ፲፫ ።

፩ ወአሚሃ መጽኡ ሰብእ ኀቤሁ ወዜነውዎ በእንተ ገሊላውያን እለ ደመረ ጲላጦስ ደሞሙ ምስለ መሥዋዕቶሙ ።

፩ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋራ የቀላቀለው የገሊላውያንን ነገር ነገሩት አንድም ሰብእ መጥተው የነገሩት ሰዎች እሉ ሐተታ ለገቢረ በዓል አልመጡም ነበርና ለበዓል ስለምን አልመጣም ብሎ በሀገራቸው መሥዋዕት ሠውተው በዓል አድርገው ሳሉ ገሥግሦ ደርሶ ፈጅቷቸዋል ። ይህማ እንዳይሆን ጲላጦስ ሮማዊ ነው እንጂ አይሁዳዊ ነውን ለሕግ ይቀናልን ብሎ ግብር አስቀርተው ነበርና በሀገራቸው መሥዋዕት ሠውተው በዓል አድርገው ሳሉ ገሥግሦ ሄዶ ፈጅቷቸዋል ይህን መጥተው ነገ

ሩት መልካም አደረገ ቢል የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ይላል የሰው ጥፋት አያሳዝነው ሲማለት መልካም አላደረገም ቢል ከጲላጦስ ጋራ ለማጣላት ነው ።

፪ ወተሠጥዎሙ እግዚእ ኢየሱስ ።

፪ ጌታም መለሰ ።

ወይቤሎሙ ይመስለክሙኑ ከመ እሙንቱ ገሊላውያን ኃጥአን እምኵሉ ሰብአ ገሊላ ።
በገሊላ ካለው ሰው ሁሉ ተለይተው እሊህ ገሊላውያን ኃጥአን ይመስሏችኋልን ።
እስመ ዛቲ ሕማም ረከበቶሙ ።
ይህች ሞት ተፈርዳባቸዋለችና ።

፫ አልቦ ። አይደለም ።

እብለክሙ እመሰ ኢነሣሕክሙ አንትሙኒ ከማሆሙ ትትኀጐሉ ኵልክሙ ።
እናንተም ንስሐ ካልገባችሁ ሁላችሁም እንደነሱ ትጠፋላችሁ ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፬ ወሚመ ይመስለክሙኑ እሉ ዐሠርቱ ወስመንቱ እለ ወድቀ ዲቤሆሙ ማኅፈድ በሰሊሆም ወቀተሎሙ ይመስለክሙኑ ከመ እሙንቱ ኃጥአን እምኵሉ ሰብአ ኢየሩሳሌም ።

፬ በሰሊሆም ግምብ ፈርሶ የገደላቸው እኒህ ዐሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ካሉ ሰዎች ሁሉ ተለይተው ኃጥአን ይመስሏችኋልን ።

፭ አልቦ ። አይደለም ።

እብለክሙ እመሰ ኢነሣሕክሙ ከማሆሙ ትትኀጐሉ አንትሙሂ ኵልክሙ ።

ካልተመለሳችሁ ሁላችሁም እንደነሣቸው ትጠፋላችሁ ብዬ እነግራችኋለሁ መከራ አንድ ጊዜ ይከተታልን ፊት የደረሰው ፊት ኋላ የደረሰው ኋላ ይከተት የለምን ሞትም እንደዚሁ ነው ። ሐተታ ይህ ግምብ ፈርሶ ሰው ያጠፋል ተብሎ ሲነገር ነበር በዝናም ጊዜ ተሰብስበው ከዚያ ገብተው ተቀምጠው ሳሉ ተጭኖ ፈጅቷቸዋል ዮሐንስ መደብር ግን በቅትለተ ሕፃናት ጊዜ የሄሮድስ ሠራዊት ተሰብስበው ገብተው እኔ ዐሥር ፈጀሁ እኔ ዐሥራ አምስት ፈጀሁ እኔ ሀያ ፈጀሁ ። የሆንኩት የለም ሲባባሉ ይህ ግምብ ፈርሶ ተጭኖ ፈጅቷቸዋል ብሏል ።

በእንተ በለስ ዘአልባቲ ፍሬ ።

፮ ወመሰለ ሎሙ ወይቤሎሙ አሐዱ ብእሲ ቦቱ በለስ ውስተ ዓጸደ ወይኑ እምርት ፣ ጸሎት መላልሶ መጸለይ እንዲገባ ፈጥኖ መተው እንዳይገባ ሲገዘው ሲያደርገው ያልወደደውን ተላጽቆት ሲሊል እንዲያስደርግለት ምሳሌ መስሎ ያመጣል ።

፮ ላንድ ሰው በወይኑ ቦታ በለስ ነበረችው ። ሐተታ አንድ ወጥ የበለስ አንድ ወጥ የወይን ይሀስ የሆነ እንደሆነ ሥሩ እየተዛመተ አያፈራም ብሎ ቀድሞ የወይን ነበር ኋላ የበለስ ሁኖዋል ፤

ወሖረ ኀቤሃ ይንሣእ ፍሬሃ ።
ፍሬ ባገኘባት ብሎ ወደሷ ሄደ ።

፯ ወኢረከበ

፯ አላገኘም

ወሶበ ኢረከበ ይቤሎ ለዓቃቤ ወይን ናሁ ሣልስየ ክረምት እንዘ እመጽእ እንሣዕ ፍሬሃ ለዛቲ በለስ ።
ባያገኝባት ለጠባቂው እንዲህ አለው ። በዚህች በለስ ፍሬ ባገኝባት ብየ ስመላለስ እነሆ ሦስት ዓመቴ ነው ።
ወኢረከብኩ ። አላገኘሁም ።
ግዝማ እንከሰ ከመ ኢታፅርዕ ምድረ ።
እንግዴህስ ወዲህ ምድራችንን እንዳታቦዝን ቁረጣት አለው ።

፰ ወአውሥአ ዓቃቤ ወይን ፤

፰ ወይን ጠባቂውም መለሰ ፤

ወይቤሎ ኅድጋ እግዚእ ሐሪፈኒ ።
አቤቱ የዘንድሮን ተዋት ።
እስከ እከሪ መሬተ ዐእወዲ ወእክዑ ድኩአ ታሕቴሃ
በሥሯ ዐፈር እስታስታቅፋት ፍግ እስካፈስባት ድረስ ።
ለእመቦ ከመ ትፈሪ ለዘይመጽእ ።
ምናልባት ለሚመጣው ዘመን ታፈራ እንደሆነ ።

፱ ወእመ አኮሰ ንገዝማ እመሐየ ።

፱ ያለዚያ ግን ብንፍር ትቆርጣታለህ አለው ። በሰው ምት ያጠራጥረዋልና አንድም አሐዱ ብእሲ ቦቱ በለስ ብለህ መልስ ብእሲ ጌታ በለስ ቤተ እስራኤል ናቸው በለስ ዘይቤ ቤተ እስራኤል እመንቱ እንዲል ሕግ በሚጠብቁበት በኢየሩሳሌም ለጌታ ቤተ እስራኤል እሉት ወሖረ ኀቤሃ በመምህራኑ ብሎት እድሮ ሃይማኖት ምግባር ባገኝባቸው ብሎ ሄደ ወኢረከበ ። ሃይማኖት ምግባር አላገኘባቸውም ወሶበ ኢረከበ ባያገኝባቸው ይቤሎ ለመጋቢሁ ። መጋቤ ብሉይ ቅዱስ ሚካኤልን ሃይማኖት ምግባር ባገኝባቸው ብየ ስመላለስ ሦስት ዓመቴ ነው ማለት ዘመነ መሳፍንት ዘመነ ነገሥት ዘመነ ክህናት ። ወኢረከብኩ አላገኘሁባቸውም ። ግዝማ እንከሰ ። አጥፋቸው ። ከመ ኢታጽርኦ ምድረ እብነት ሁነው ሌላውን እንዳያስጎዱ አለው ። ወአውሥአ ወይቤሎ አቤቱ የዘንድሮን ይቅር በላቸው እስከ እከሪ መሬተ ተራድቼ ሥራ እስኪሠሩቸው ድረስ ። ለእመቦ ከመ ትፈሪ ለዓም ምናልባት ለሚመጣው ዘመን ሃይማኖት ቢይዙ ምግባር ቢሠሩ ወእመ አኮሰ ። ያለዚያ ግን እናጠፋቸዋለን ። እመ ሐየሰ መቼም ሙቶ ነዋሪዎች ናቸው አንድም መልስ በለስ ቤተ እስራኤል ናቸው እዩ

ዕዋጥም ከብት ቢሉ በልጁ ሠለው ሠጥ ወልድ ቢሉ ሰው ሁና ሃይማኖት ምግባር እገኝባችዋለሁ ብሎ ወደ እስራኤል ሄደ ። ወኢረከበ አላገኘባቸውም ወሶበ ኢረከበ ባያገኝባቸውም ይቤሎ ለመጋቢሁ ። መጋቢ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤልን ምግባር ሃይማኖት ባገኝባቸው ብዬ ስመላለስ ዛሬ ሦስት ዓመቴ ነው እሁን የተመቸ ጌታ ያስተማረ ሦስት ዓመት ነውና ወኢረከብኩ ። ሃይማኖት ምግባር አላገኘሁባቸውም ። ግዝማ እንከሰ ከመ ኢታጽርዕ ምድረ ። አብነት ሆነው ሌላውን እንዳያስጉዱ እጥፋቸው አለው ። ከዚህ በታች አይለወጥም እንድም መልስ ብእሲ አይለወጥም ጌታ ነው ። ሕግ በሚጠብቁበት ፀኢያሩሳሌም ለጌታ ምእመናን አሉት ። ወሐረ ኀቤሃ በመምህራን ሐዲስ አድሮ ሃይማኖት ምግባር አገኝባቸዋለሁ ብሎ ሄደ ።

አላገኘባቸውም ወሶበ ኢረከበ

ሃይማኖት ምግባር ባያገኝባቸው መልአከ ዑቃቢውን መምህረ ንስሐውን ሃይማኖት ምግባር ባገኝባቸው ብየ ስመላለስ ሦስተኛ ዓመቴ ነው ማለት ሕፃንነት ውርዝውና ዕርግና። ወኢረከብኩ፣ እላገኘሁባቸውም። ግዝማ ። መልአከ ዑቃቢውን እጥፋቸው አብነት ሁነው ሌላውን እንዳያስጎዱ አለው ።

መምህረ ንስሐውን አውግዘህ ለያቸው አለው ። መልአከ ዑቃቢው የዘንድሮን ተዋቸው ተፋድቼ ሥራ እስኪሠራቸው ድረስ ። ለአመበ ፡ ምናልባት ለሚመጣው ዘመን ሃይማኖት ቢይዙ ምግባር ቢሠሩ ወእመ አኮሰ ንገዝማ ፡ ያለዚያ ግን እናጠፋቸዋለን ። እመ ሐዮነ ። መችም መች ነዋሪዎች ነንና መምህረ ንስሐው የዘንድሮን ተዋቸው መከሬ አስተምሬ ሃይማኖት እስካስይዛቸው ምግባር እስካሠራቸው ድረስ ምናልባት ለሚመጣው ዘመን ሃይማኖት ቢይዙ ምግባር ቢሠሩ ያለዚያ ግን አውግዘን እንለያቸዋለን እመ ሐዮነ ባንሞት በሰው ሞት ያጠራጥራል ።

በእንተ ብእሲት ዘድኅነት በዕለተ ሰንበት ።

፲ ወእንዘ ይሜህሮሙ በሰንበት በ፩ ምኵራብ ።
፲ ቅዳሜ ባንድ ምኩራብ ሲአስተምራቸው ።

፲፩ ወሀለወት ብእሲት እንተ አድወያ ጋኔን ፲ ወ፰ ዓመተ ፤

፲፩ ሰይጣን ዐሥራ ስምንት ዓመት እንድትታመም ያደረጋት ሴት ነበረች ። ወጥሕቁት ኅባጣም ነበረች ። እንድም ወጥሕቁት እንተ አድወያ ጋኔን ወእንተ ጥሕቁት በል ። ወኢትክል ቀዊመ ግሙራ ። ቀንቶ መሄድ አይቻላትም ነበር ።

፲፪ ወርእያ እግዚእ ኢየሱስ ።
፲፪ ጌታም አያት ።
ወመሐራ ። እዘነላት ።
ወጸውዓ ወይቤላ አ ብእሲቶ ተፈታሕኪ እም ደዌኪ ።

ጠርቶ አንቺ ሴት ከደዌሽ ተለይተሻል አላት ። ሐተታ ተፈታሕኪ ማለቱ ግን እንደተቋጠረ እቅማጸ አድርጓት ነበርና ።

፲፫ ወአንበረ እዴሁ ላዕሌሃ ።
፲፫ እጁን በላይዋ ጫነባት ።
ወረትዓት ሶቤሃ ። ፈጥና ቀናች ።
ወእዕኰተቶ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርንም አመሰገነች ።
ከደዌዬ የፈወስኸኝ ከዚህ ያደረስከኝ ብላ ።

፲፬ ወአውሥአ መጋቤ ምኵራብ እንዘ ይትመዓዕ ።

፲፬ የምኩራቡ ሹም ተበሳጭቶ ተናገረ ።
እስመ በሰንበት ፈወሰ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታም ቅዳሜ ፈውሿልና ።
ወይቤሎሙ ለሕዝብ እኮኑ ሰዱስ መዋዕል ዘትትገበሩ ግብረክሙ ቦቶን ።
ሥራችሁን የምትሠሩባቸው ስድስት ዕለታት ያሉላችሁ አይደለምን ።
ውእተ አሚረ ንዑኬ ተፈወሱ በውእቶን ዕለታት።
ያን ጊዜ መጥታችሁ ተፈወሱ ።
ወአኮ በዕለተ ሰንበት ።
በሰንበት ግን ልትፈወሱ አይገባም አላቸው ። ሐተታ እንዲህ ያሏቸው እንደሆነ ለሥራቸው ሲሳሱ ይቀራሉ ፡ ተአምራት አይደረግም ሰው አይሳብም አሪት አትጠፋም ወንጌል አትሰፋም ብሎ ነው ።

፲፭ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፲፭ ጌታችን ኢየሱስም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ።
እንዲህም አላቸው ።
አ መደልዋን ፡
እናንተ ግብዞች ።
እንትሙሰ ኢትፈትሑኑ እድገክሙ ወላህሚክሙ እምነ ምቅማሁ ወኢትወስድዎኑ ታስትይዎ ማየ በዕለተ ሰንበት ።

እናንተስ አህያችሁን በሬያችሁን በሰንበት ገለባ ከሚበላበት ፈትታችሁ ውኃ ልታጠጡት ትወስዱት የለምን ፤

፲፮ ወዛቲ ወለተ አብርሃም እንተ አሰራ ሰይጣን ፲ተ ወ፰ተ ዓመተ አኮኑ ርቱዕ ትትፈታሕ እምነ ማእሰራ ይእቲኒ በዕለተ ሰንበት ፡

፲፮ ያንማ እንዲታ በውኃ ጥም ይሙቱን ትሉኝ እንደሆነ ፡ ሰይጣን ዐሥራ ስምንት ዓመት እንድ

ትታመም ያደረጋት ይህችስ የአብርሃም ልጅ ከደዌ ማሰሪዋ ልትፈታ አይገባምን አላቸው ።

፲፯ ወሶበ ተናገረ ዘንተ ተኃፍሩ ኵሎሙ እለ ቆሙ ላዕሌሁ ።

፲፯ ይህን በተናገረ ጊዜ በጠላትነት የተነሡበት ሁሉ ምላሽ አጡ ።
ወተፈሥሑ ኵሉ ሕዝብ በእንተ ኵሉ መንክር ሠናይ ዘይትገበር እምኔሁ ላዕሌሁ ።
በሱ ሥልጣን ስለ ሚያደርገው ተአምራት ሕዝቡ ሁሉ ደስ ብሏቸው አደነቁ ።

በእንተ ኅጠተ ሰናፔ ወበእንተ ዘርዕ ወብኁእ

፲፰ ወይእተ ዕለተ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ምንተ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ።

፲፰ ይህ ሰው እንዲህ ማለቱ እንዴህ ያልኋቸው እንደሆነ ስለሥራቸው ሲላሉ ይቀራሉ ተአምራት አይደረግም ሰው አይሳብም ኦሪት አትጠፋም ወንጌል አትስፋም ብሎ እንጂ ነው ።
ወንጌልማ ትጠፋ ዘንድ ምን ትመስላለች ።
ወበምንት እስተማስላ ።
በምንስ እመስላታለሁ ።

፲፱ ትመስል ኅጠተ ሰናፔ እንተ ነሥአ ብእሲ ወዘርዓ ውስተ ገራህቱ ።

፲፱ ሰው በርሻው ውስጥ የዘራትን ሰናፍጭ ትመስላለች ።
ወልሕቀት ። አደገች ።
ወኮነት ዕፀ ዓባየ ። ታላቅ ዛፍ ሆነች ።
ወአጽለሉ አዕዋፈ ሰማይ ውስተ አዕጹቂሃ ።
ወፎችም መጥተው ተቀመጡባት ።

፳ ወካዕበ ይቤ በምንት አስተማስላ ለመንግሥተ እግዚአብሔር

፳ ዳግመኛ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን እመስላታለሁ ።

፳፩ ትመስል ብሑአ ዘነሥአት ብእሲት ።
፳፩ ሴት የወሰደችውን እርሾ ።
ወኀብአቶ ውስተ ሠለስቱ መሥፈርተ ሐሪጽ ።
ሦስት መስፈሪያ ዱቄት የለወሰችውን ።
ወእስከ አብኀአ ኵሎ ።
ሁሉን መጣጣ ያደረገ እርሾን ትመስላለች ።

በእንተ ትልቁ ኅሩያን ።

፳፪ ወኮነ የሐውር አህጉረ ወአዕጻዳተ ወያንሶሱ በኢየሩሳሌም ወይሜህር ።

፳፪ በየሀገሩና በየአውራጃው በኢየሩሳሌምም እየተመላለሰ ያስተምር ነበር ።

፳፫ ወይቤሎ አሐዱ ብእሲ እግዚኦ ውሑዳን እንጋ እሙንቱ እለ ይድኅኑ ።

፳፫ [illegible] ቢልበት ከነሱ አንዱ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው አለው ።
፳፬ ወይቤሎሙ ተጋየሉ ትባኡ እንተ ጸባብ አንቀጽ ።

፳፬ በጠባቢቱ ደጅ ለመግባት ድል ንሡ አላቸው ። አንድም ሕጉን ለመጠበቅ ተበረታቱ ።
እብለክሙ ብዙኃን እለ የኃሥሡ ይበኡ ።
ሊገቡ የሚወዱ ብዙ ናቸው ወኢይክሉ እይቻላቸውም ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፳፭ እስመ ይትነሣእ በዓለ ቤት ወየአጹ ኆኅቶ ማቴ ፳፭ ፥ ፲፩ ።

፳፭ ባለቤት ተነሥቶ ደጁን ይዘጋልና ማለት እምኤኤ ዓለማት ጌታ ምሕረት ይከለክላልና ።
ወይእተ ጊዜ ትቀውሙ አፍአ ወትጐድጒዱ ።
ያን ጊዜም ከውጪ ቆማችሁ ደጅ ትመታላችሁ ።
እንዘ ትብሉ እግዚኦ እግዚኦ አርኅወነ ።
አቤቱ አቤቱ ክፈትልን እያላችሁ ።
ወያወሥእ ወይብለክሙ ኢያአምረክሙ እምአይቴ አንትሙ ።
ከወዴትም እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም ብሎ ይመልስላችኋል ።

፳፮ ወእምዝ ትእኅዙ ትብልዎ በላዕነ ወሰተይነ በቅድሜከ ።

፳፮ ከዚህ በኋላ ከፊትህ ስንበላ ስንጠጣ አልነበረምን ።
ወመሀርከ በመራህብቲነ ።
ባደባባያችንስ ስታስተምር አልነበረምን ትሉ ትጀምራላችሁ ።

፳፯ ወይቤለክሙ ኢየአምረክሙ ። ማቴ ፯ ፳፫ መዝ ፮ ፥ ፰ ።

፳፯ ዐላውቃችሁም ይላችኋል ።
ረኃቁ እምኔየ ገበርተ ዓመፃ ።
ግፍ የምታደርጉ ሁሉ ከኔ ራቁ

፳፰ ወሀሎ ውስተ ብካይ ወሐቅየ ስነን ።
፳፰ ሐዱ ልቅሶ ጥርስ ማፋጨትም ወዳለበት ወእመ ርኢክሙ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ወለኵሎሙ ነቢያት እንዘ ይረፍቁ በመንግሥተ እግዚአብሔር ።

አብርሃምን ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በመንግሥተ ሰማይ ባያችኋቸው ጊዜ ።
ለክሙሰ ያወፅኡክሙ አፍአ ።
እናንተን ግን ከመንግሥተ ሰማይ ውጭ ያወጧችኋል ።

፳፱ ወይመጽኡ እምጽባሕ ወእምዕራብ ወእም ሰሜን ወእምደቡብ ።

፳፱ ከምሥራቅ ከምዕራብ ከሰሜን ከደቡብ መጥተው ።

ወይትፌሥሑ በመንግሥተ እግዚአብሔር ።
በእግዚአብሔር መንግሥትም ተድላ ያደርጋሉ ።

፴ ወይከውኑ ቀደምት ደኃርተ ።
ማቴ. ፲፱ ፡ ፴ ማር . ፲ ፡ ፵ ።

፴ ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ ።

ወደኃርት ቀደምት ።
ኋለኞችም ፊተኞችን ይሆናሉ

በእንተ ጽልዕ ዘሄሮድስ ።

፴፩ ወበይእቲ ዕለት መጽኡ ሰብእ እምፈሪሳውያን ።

፴፩ በዚያች ቀንም ከፈሪሳውያን ወገን መጥተው።

፴፪ ወይቤልዎ ፃዕ ወሑር እምዝየ እስመ ሄሮድስ የኀሥሥ ወይፈቅድ ይቅትልከ ።

፴፪ ሄሮድስ ሊገድልህ ይሻልና ከዚህ ሂድ አሉት። ሐተታ ለሱ [illegible] ከዚህ ያስተጓጉሉ እንደሆነ ተአምራት [illegible] ትመፋለት ወንጌል ትሰፋለች [illegible] ነው እንጂ ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ሑሩ በልዋ ለዛቲ ቍንጽል ።
ያችን ቀበሮ ሄዳችሁ እንዲህ በሏት ።
ናሁ አወፅእ አጋንንተ ።
እነሆ አጋንንትን አወጣለሁ ።
ወእሁብ ሕይወተ ።
ድውይንም እፈውሳለሁ ።
ዮም ።
የነገሩት በመጀመሪያ ዓመት ነው ያሉ እንደሆነ ።
ዮም በመጀመሪያው ዓመት ።
ወጌሠመ ።
በሁለተኛው ዓመት ።
ወበሣልስት ዕለት እፌጽም ።
በሦስተኛውም ዓመት እፈጽማለሁ ማለት እሞታለሁ ። እንድም በሁለተኛው ዓመት ነው ያሉ እንደሆን ዮም በሁለተኛው ዓመት ጌሠም በሦስተኛው ዓመት ድውይ እፈውሳለሁ ጋኔን አወጣለሁ ። ወሣልስት በሦስተኛው ጊዜ እሞታለሁ ።

፴፫ ወባሕቱ ዮምሰ ወጌሠመ ሀለውኩ ።
፴፫ ነገር ግን ዛሬና ነገ እኖራለሁ ።
ወበሣልስት እሐውር ።
በሦስተኛውም ዓመት እሞታለሁ ።
እስመ ኢይደልዎ ለነቢይ መዊት በአፍኣ ዘእንበለ በኢየሩሳሌም ።

ለነቢይ ለክርስቶስ በኢየሩሳሌም እንጂ ከኢየሩሳሌም ውጭ ተሰቅሎ መሞት አይገባውምና ። ሐተታ በኢየሩሳሌም መሰቀሉ ስለ ምን ነው ቢሉ ወገብረ መድኃኒተ በማእከለ ምድር ያለው ትንቢት ሊፈጸም አንድም ርእሰ አዳም ከዚያ አለና እሱን ከማዳን እንደ መጣ ለማጠየቅ አንድም አዳምን ያሳተ ርእሰ አርዌ ከዚያ ወድቆ ነበርና ያን ለማጥፋት እንደመጣ ለማጠየቅ ።

ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ ተኃድጎታ ለኢየሩሳሌም ።

፴፬ ወይቤ ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም እንተ ትቀትሎሙ ለነቢያት ። ማቴ. ፳፫ ፡ ፴፯ ።

፴፬ ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ አንች ነቢያትን ገዳይ ።
ወትዌግሮሙ ለሐዋርያቲሃ እለ ተፈነዉ ሀቤሃ ።
ወዳንች የተላኩትንም ሐዋርያት የምትወግሪ ።
ሚመጠነ ፈቀድኩ እስተጋብኦሙ ለደቂቅኪ ከመ እንተ ታስተጋብእ ዶርሆ ዕጕሊሃ ታሕተ ክንፊሃ ።
ዶሮ ልጆችዋን በክንፏ እንድትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ምን ያህል ወደድኩ ።
ወአበይክሙ ። እምቢ አላችሁ ።

፴፭ ወናሁ ይትኃደግ ለክሙ ቤትክሙ በድወ ።
፴፭ እነሆ ቤታችሁ ፈርሶ ይቀርላችኋል ። እብለክሙ ከመ ኢትሬእዩኒ እምይእዜ እስከ ሶበ ትብሉ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ። በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስከ ትሉ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

ምዕራፍ ፲፬ ።

ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ ለቅብዉ በዕለተ ሰንበት ።

፩ ወእምዝ ሶበ ሖረ ቦአ ቤተ አሐዱ ብእሲ እምነ መላእክቲሆሙ ለፈሪሳውያን በሰንበት ከመ ይብላዕ እክለ ።

፩ ከዚህ በኋላ በሄደ ጊዜ እህል ይበላ ዘንድ ከፈሪሳውያን አለቆች ወዳንዱ ቤት በሰንበት ገባ ።
ወእሙንቱሰ ይትዓቀብዎ ።
እነሱም ይጠባበቁት ነበር ።

፪ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ቅብው ቅድሜሁ ።
፪ ሆዱ የተነፋ ሰው በፊቱ ነበር ።
ቅድሜሁ ሀሉ ሀሉ ቅድሜሁ ብለህ ግጠም ።

፫ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ
፫ ጌታም መለሰ ።

ወይቤሎሙ ለጸሐፍት ሀፃሮ ወለፈሪሳውያን ይከውንሁ በሰንበት ፈውሶ ወሚመ ኢይከውንሁ ።
በሰንበት ድውይ መፈወስ ይገባልን ወይም አይገባም ብሎ የገር ጸሐፊዎችንና ፈሪሳውያንን ጠየቃቸው ።

፬ ወአርመሙ ዝምም አሉ ።
ወነሥኦ ወፈወሶ ወፈነዎ ።
ወሰዶ ፈውሶ ሰደደው ።

፭ ወእምዝ ይቤሎሙ እመቦ አሐዱ እምኔክሙ ዘወድቆ ላህሙ አው አድጉ ውስተ አዘቅት ።

፭ ከእናንተ [illegible] በሬው ወይም አህያው ጉድጓድ ቢወድቅበት ።
አኮኑ በጊዜሁ ያነሥኦ ወያወፅኦ በዕለተ ሰንበት ።
በሰንበት ያን ጊዜውን ያነሣው የለም አላቸው ።

፮ ወስአኑ አውሥኦቶ በእንተ ዝንቱ ነገር ።
፮ ስለዚህ ነገር መመለስ ተሳናቸው ።

ዘከመ መሀረ ኢየሱስ ትሕትና ወፍቅረ ለእለ ይረፍቁ ።

፯ ወመሰሎሙ ሎሙ ወይቤሎሙ ለእለ ሀለዉ ውስተ ምሳሕ ።

፯ በምሳ ላሉ ምሳሌውን መስሎ ነገራቸው ።
ወመሀሮሙ ሶበ ርእዮሙ እንዘ ይትባደሩ ውስተ ርእሰ ምርፋቅ ።
በላይ ለመቀመጥ ሲቀዳደሙ ባያቸው ጊዜ ምንጣፍ መጨጊያ ካለበት ጽዋ ከሚጀመርበት እንጀራ ከበዛበት ወጥ ከተደራረበበት ሲቀዳደሙ ባያቸው ጊዜ ።

፰ ወይቤሎ ።
፰ እንዲህም አላቸው ።
እመቦ ዘጸውዓከ ውስተ ምሳሕ ኢትርፋቅ ውስተ ርእሰ ምርፋቅ ክቡር ።
ለምሳ የጠራህ ሰው ቢኖር ከራስጌ አትቀመጥ ።
ዮጊ ይመጽእ ዘይከብረከ ።
ወይም ካንተ የበለጠ ይመጣ ይሆናል ።

፱ ሕሊመ መጺአ ድኅረ ይብለከ ዝኩ ዘጸውዓከ ኅድግ ሎቱ ዘንተ ገጸ ።

፱ ያ የጠራህ ኋላ መጥቶ ይህን ሥፍራ ለእንግዳ ተውለት ይልሃልና ።
ወትትኃፈር ውእተ ጊዜ ወትቀርድ ውስተ ምርፋቅ ዘይቴሐት ።
ያን ጊዜም አፍረህ ከታችኛው መቀመጫ ትወርዳለህ ።

፲ ወእመሰ ሶበ ዘጸውዓከ ። ምሳ. ፳፭ ፡ ፮-፯ ።
፲ የጠራህ ሰው ቢኖር ።
ሑርከ ። አንተም ብትሄድ ርፍቅ ውስተ ታሕታይ ምርፋቅ ።
ከታች መቀመጫ ተቀመጥ ።
ከመ ሶበ መጽአ ዘጸውዓከ ይበልከ አርኅቅ ዕርግ ውስተ ዘይትሌዓል ምርፋቅ ።
የጠራህ ሰው በመጣ ጊዜ ወዳጄ ከዚህ ወደላይ ወጥተህ ተቀመጥ ይልህ ዘንድ ።
ወውእቱ ጊዜ ይከውንከ ክብረ በቅድመ ኵሎሙ እለ ይረፍቁ ወይመስሑ ምስሌከ ።
ያን ጊዜም ካንተ ጋራ ተቀምጠው የሚበሉት ሁሉ ያከብሩሃል ።

፲፩ እስመ ኵሉ ዘአዕበየ ርእሶ የኃሥር ። ማቴ. ፳፫ ፡ ፲፪ ሉቃ. ፲፰ ፡ ፲፬ ።

፲፩ ራሱን ያከበረ ሁሉ ይዋረዳልና
ወዘአትሐተ ርእሶ ይከብር ።
ራሱንም ያዋረደ ይከብራልና ።
ወይቤሎ ለዘጸውዖ ።
ለጠራውም ሰው እንዲህ አለው ።

፲፪ ሶበ ትገብር በዓለ ወምሳሐ አው ድራረ ። ምሳ ፡ ፫ ፡ ፱ ።

፲፪ በዓልም በምታከብርበት ምሳም በምታቀርብበት ዝክርም በምትዘክርበት ጊዜ ።
ኢትጸውዕ ፡ አዕርክቲከ ወአኃዊከ ።
ወንድሞችህንና ወዳጆችህን አትጥራ ።
ዘአዝማዲከ ወጐረከ ወማኅፈረከ ።
ዘመዶችህንና ጎረቤቶችህን ።
ወቢጸከ አብዕልተ ።
ባለጠጎችን ።
ከመ ይጼውዑከ እሙንቱሂ ።
እርሳቸውም ይጠሩህ ዘንድ ።
ወይከውንከ ፍዳ በነቢሆሙ ።
ብድራት ይሆንብሃልና ።

፲፫ አላ አንተሰ ሶበ ትገብር በዓለ ወምሳሐ ጦቢ ፡ ፬ ፡ ፯ ።

፲፫ ዝክር በምትዘክርበት ምሳ በምታቀርብበት ጊዜ ።
ጸውዕ ነዳያን ወምስኪናን ።
የተቸገሩትንና ድሆችን ጥራ ።
ወፅውሳነ ። ዕውራንን ።
ወስቡራነ ። አንካሶችንም ።

፲፬ ወብፁዕ አንተ ።
፲፬ እንዲህ ያደረግህ እንደሆን የተመሰገንክ ነህ
እስመ አልቦሙ ዘይፈድዩከ ።
የሚከፍሉህ የላቸውምና ።
ባሕቱ ትትዓሠይ አመ ይትነሥኡ ጻድቃን ።
ጻድቃን በሚነሡበት ቀን ዋጋህን ታገኛለህ እንጂ ።

፲፭ ወሰሚዖ ዘንተ አሐዱ እምእለ ይረፍቁ ። ይቤሎሙ ብፁዕ ውእቱ ዘይበልዕ እክለ በመንግሥተ ሰማያት ።

፲፭ ከተቀመጡት አንዱ ይህን ሰምቶ በመንግሥት ሰማይ እህል የሚበላ ሰው የከበረ ነው አለ ። የእንብላው መጣፍ የጅብ መጣፍ እንዲሉ ። በዚህ ዓለም እህል ትምህርትን የሚመገብ ሰው በመንግሥት ሰማይ ንዑድ ክቡር ነው ። አንድም ወመሰለ ሎሙ ብለህ መልስ ። በትምሀርት ሳሉ ምሳሌ መስሎ ነገራቸው ለማስተማር ሲቀዳደሙ ባያቸው ጊዜ ። ወይቤሎሙ በትምህርት የጠራህ ሰው ቢኖር አስተምራለሁ አትበል ዮጊ ይመጽእ ወይም የተማረ ካንተ የበለጠ ይሆናል እስመ መጺእ ፡ የጠራህ ሰው መጥቶ ማስተማሩን ለእገሌ ተውለት ይልሃልና ፡ ወትትኀፈር ያን ጊዜ እፍረህ ወደትምህርት ትመለሳለህ ። ወእመሰ ቦ ወደመምርት የጠራህ ሰው ቢኖር ወሖርከ ፡ አንተም ብትሄድ ፡ ርፍቅ ውስተ ታሕታይ ምርፋቅ እማራለሁ በል ፡ ከመ ሶበ መጽአ የጠራህ ሰው ወዳጄ መማሩ ይበቃሃል አስተምር ይልህ ዘንድ ወውእቱ ጊዜ ይከውንከ ክብረ ያን ጊዜ በሁሉ ዘንድ ክብር ይሆንልሃል ። እስመ ኵሉ ራሱን ያከበረ ይዋረዳልና አስተምራለሁ አትበል ወዘአትሐተ ርእሶ ራሱን ያዋረደ ይከብራልና እማራለሁ በል ። ወይቤሎ ለዘጸውዖ ። በምታስተምርበት ጊዜ የተማሩትን አስተምራለሁ አትበል ።

ከመ ይጸውዑከ ። ያስተምሩህ ዘንድ ። ወይከውንከ ፍዳ ። ብድራት ይሆንብሃልና አላ ሶበ ትገብር ። በምታስተምርበት ጊዜ ያልተማሩትን አስተምር እንጂ ወብፁዕ ። እንዲህ ያደረግህ እንደሆን የተመሰገንክ ነህ።እስመ አልቦሙ ፡ የሚያስተምሩህ የላቸውምና ። ወባሕቱ ጻድቃንዋጋቸውን በሚያገኙበት ጊዜዋጋህን ታገኛለህ እንጂ ነገር ግን ዋጋህን ታገኛለህ አንድም ወመሰለ ሎሙ ብለህ መልስ በምናኔ ላሉ ምሳሌ መስሎ ነገራቸው ፡ ሶበ ርእዮሙ ፡ ለተባሕትዎ ሲቀዳደሙ ባያቸው ጊዜ ይቤሎሙ ፡ ወደምናኔ የጠራህ ሰው ቢኖር ተባሕትዎ እይዛለሁ እዘጋለሁ አትበል ፡ ዮጊ ወይም ካንተ የበለጠ የረዳ ይኖራል ፡ እስመ መጺእ ። ወደምናኔ የጠራህ መጥቶ ተባሕትዎውን ለእገሌ ተውለት ይልሃልና ፡ ወውእቱ ጊዜ፡ ያን ጊዜ እፍረህ ልርዳ ትላለህና ፡ ወደመርዳት ትመለሳለህ ፡ ወያወፅእዎ ዘበእሒሥሮት እንዲል ፡ ሳይረዳ የዘጋውን ያስወጡታል ፡ ወእመሰቦ የጠራህ ሰው ቢኖር ። ወሖርከ ፡ አንተም ብትሄድ ። ርፍቅ እረዳለሁ በል ። ከመ ሶበ መጽአ ። ወደምናኔ የጠራህ ሰው ርዳታው ይበቃሃል ተባሕትዎ ያዝ ይልህ ዘንድ ወውእቱ ጊዜ ያን ጊዜ በሁሉ ዘንድ ክብር ይሆንሃል ። እስመ ኵሉ ዘአዕበየ ። አይለወጥም ወይቤሎ ። ብምትመንንበት ጊዜ የተማሩትን ይዤ እመነናለሁ አትበል ከመ እሙንቱኒ ግርማ ሌሊቱ ድምፀ አራዊቱ ፀዐገ ገዳሙ እንደምን ይቻላል እያሉ ይከራከሩሃልና ፡ አላ ሶበ ትገብር ። ወደምናኔ በምትጠራበት ጊዜ ያልተማሩትን ይዘህ መንን እንጂ ። ይኄይስ ብእሲ ዘጠበ በለቢሰ ምግባራት እምነ ብእሲ በዓለ ኃሠሣ ወንጽር እንዲል ። ወብፁዕ አንተ እንዲህ የሆነ እንደሆን ንዑድ ክቡር ነህ ። እስመ አልቦሙ ያሰብከውን አይከራከሩህምና አያስቀሩብህምና ወሰሚዖ አይለወጥም ።

በእንተ ምሳሌ ዘዕሱራን ።

፲፮ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አሐዱ ብእሲ ገብረ ምሳሐ ዓቢየ ። ማቴ . ፳፪ ፡ ፪ ራእ . ፲፱ ፡ ፱ ።

፲፮ አንድ ሰው ታላቅ ምሳ አደረገ ።
ወዓሥርሙ ለብዙኃን ።
ብዙ ሰዎችንም ጠራ ።

፲፯ ወሶበ በጽሐ ዓሥር ፈነወ ገብሮ ይጸውዮሙ ለእለ ተኣሥሩ ።

፲፯ የታደሙበት ቀን በደረሰ ጊዜ የታደሙትን ይጠራ ዘንድ ባሪያውን ላከ ።
ወሖረ ገብሩ ወይቤሎሙ ለእለ ዓሠርዎሙ ንዑ
እስመ ናሁ ወዳእነ አስተዳለውነ ምሳሐ ።
ሂዶ ምሳውን አዘጋጅተን ፈጽመናልና ኑ አላቸው ።
ወዓበይዎ ኵሎሙ ጽቡረ ።
ሁሉም ባንድ ቃል እንቢ አሉ ።

፲፰ ወይቤሎ ቀዳማዊ ገራኅተ ተሣየጥኩ ።
፲፰ የፊተኛው ምድር ገዝቻለሁ ።
ወእጽሕቅ እሑር እርኦያ ።
ልመራት እወዳለሁ ።
ወበሎ ረሲ ሊተ ከመ ዘኢእበይኩ ።
ስለዚህ መምጣት አይቻለኝምና ከመጣሁ ቍጠር
ልኝ በለው አለው ፡

፲፱ ወይቤሎ ካልኡኒ ኃምስተ ጽምደ አልህምት ተሣየጥኩ ።

፲፱ ሌላውም አምስት ጽምድ በሮች ገዝቻለሁ ። ክልኤተ ጽምደ አኃ ይላል ሁለት ወይፈን ገዝቻለሁ ።
ወእሐውር እርእዮሙ ወእፍትኖሙ ።
ልፈትናቸውም እሔዳለሁ ፡
ወበሎ ረሲ ሊተ ከመ ዘመጻእኩ ወኢዓበይኩ ።
ከመጣሁ ቁጠርልኝ በለው አለው ።

፳ ወሚልሰኒ ይቤሎ ብእሲተ አውሰብኩ ።

፳ ሦስተኛውም ሚስት አግብቻለሁ ። ወበእንተዝ ኢይክል መጺአ ወረሲ ሊተ ከመ ዘኢ ዓበይኩክ ስለዚህም መምጣት አይቻለኝም ከመጣሁ ቊጠርልኝ በለው አለው ። ሐተታ ገራህተ ተሣየጥኩ፥ ማለታቸው ሰማያዊ ልደቱን ቢነግሯቸው እኛስ ምድራዊ ልደቱን እናውቃለን እንጂ ሰማያዊ ልደቱን እናውቅም ማለታቸውን መናገር ነው ፤ ኃምስተ ጽምደ አልህምት ማለታቸው በኀቱም ድንግል ተፀንሶ በኀቱም ደንግልና መወለዱን ቢነግራቸው እኛስ እምስቱ ሕዋሳቶች ካምስቱ ሕዋሳቶቹ አንድ ሁኖ የሚወለዱትን ልደት ነው እንጂ በኀቱም ድንግልና ተፀንሶ መወለዱን እናወቅም ማለታቸውን መናገር ነው ፤ ጽምደ አኃ ማለታቸው አምስቱን አዕማደ ምሥጢር ቢነግሯቸው በሁለቱ ጽላት የተጻፉትን ሕገጋት እንጂ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር እናውቅም ማለታቸውን መናገር ነው ። ብእሲተ አውሰብኩ ማለታቸው እንበለ ዘር መወለዱን ቢነግራቸው እኛስ በዘር በሩካቤ የማወለደውን እናውቃለን እንጂ እንበለ ዘር የሚወለደውን ልደት እናውቅም ማለታቸውን መናገር ነው ።

፳፩ ወገብአ ዝኩ ገብሩ ወነገሮ ከመዝ ለእግዚኡ ።

፳፩ ባሪያውም ተመልሶ ይህን ለጌታው ነገረው ።

ወእምዝ ተምዓ በዓለ ቤት ይእተ ጊዜ ።

ያን ጊዜም ባለቤቱ ተቆጣ ።

ወይቤሎ ለገብሩ ሑር ወፃእ ፍጡነ ውስተ መራህብት ወውስተ አስኳተ ሀገር ።

ባሪያውንም አለው ፈጥነህ ወደዐደባባይ ሂድ ።

ጸውዕ ወአምጽእ ሊተ ዝየ ነዳያነ ወፅኑሳነ ።

የተቸገሩትንና ድኆችን ።

ወዕውራነ ። የታወሩትን ።

ወስቡራነ እንካሶችን አምጣልኝ አለው ።

፳፪ ወይቤሎ ገብሩ ገበርኩ እግዚኦ በከመ አዘዝከኒ ።

፳፪ ከዚህ በኋላ ባሪያው አቤቱ እንዳዘዝከኝ አደረግሁ አለው ።

ወዓዲ ቦ መካን ።

ደግሞም ስፍራ አለ አለው ። ሐተታ የሚገባ በችቶ ከተገኘ እስመከልከለን መናገር ነው

፳፫ ወይቤሎ እግዚኡ ለገብሩ ሑር ፍጡነ ውስተ ፍናው ወውስተ ጥቅመ ሀገር ወበግብር አብእ ሰብአ ።

፳፫ ጌታውም ባሪያውን ወደቅጥርና ወደ መንገድ ውጣና የግድ አስገባ ።

ከመ ይምላእ ቤትየ ።

ቤቴ ይመላ ዘንድ አለው ።

፳፬ እብለከሙ ከመ አሐዱሂ እም እለ ተዓሥሩ እለ ጸዋዕኩ ኢይጥዕምዋ ለበዓልየ ።

፳፬ ከነዚህ ከተጠሩት ሰዎች አንዱ ስንኳ እንጀራዬን አይቀምሳትም ብየ እነግራችኋለሁ ። እልቦ ዘይጥዕም ለበዓልየ አሐዱሂ ኢይጥዕም ለበዓልየ ይላል ። እንደዚህም ሁሉ ትንቢት ከተነገረላቸው ተስፋ መስቀልን ካናገርንላቸው አንድ ስንኳ እንዳይገባ በውነት እነግራችኋለሁ ።

እስመ ብዙኃን እሉራን ወኅዳጣን ኅሩያን ።

የታደሙ ብዙ ናቸውና ። የተመረጡ ጥቂት ናቸውና ።

ዘከመ ይደሉ ተሊዎተ ኢየሱስ

፳፭ ወእምዝ እንዘ የሐውሩ ምስሌሁ ብዙኃን ሰብእ ተመይጠ ወይቤሎሙ ።

፳፭ ከዚህ በኋላ ብዙ ሰዎች ከርሱ ጋራ ሲሄዱ ተመልሶ እንዲህ አላቸው ።

፳፮ ዘይመጽእ ኀቤየ ። ማቴ. ፲ ፥ ፴፯ ።

፳፮ ወደኔ የሚመጣ ።

ወዘይፈቅድ ይትልወኒ ።

ሊከተለኝም የሚወድ

ወዘኢጸልአ አባሁ ወእሞ ።

እናት አባቱን ያልጠላ ።

ወብእሲቶ ፥	ሚስቱን ።
ቤቶ ።	ቤቱን
ወውሉዶ ።	ልጆቹን
ወአኃዊሁ ።	ወንድሞቹን
ወአኃቲሁ ።	እኅቶቹንም የማይጠላ

ወዓዲ ነፍሶሂ እንቲአሁ ።

ደግሞም ነፍሱን የማይጠላ ።

ኢይክል ከዊነ ረድዕየ ።

የኔ ደቀ መዝሙር መሆን አይቻለውም ።

፳፯ ዘኢይጸውር መስቀለ ሞቱ ወኢይመጽእ ይትልወኒ ኢይክል ከዊነ ረድዕየ ። ማቴ. ፲ ፴፰ ማር. ፰፥ ፴፬ ።

፳፯ መስቀሉን ተሸክሞ የማይከተለኝም የኔ ደቀ መዝሙር መሆን አይቻለውም ።

፳፰ ወእመቦ አሐዱ እምኔክሙ ዘይፈቅድ ይሕንጽ ማኅፈደ ።

፳፰ ከናንተ ወገን ግምብ ሊሠራ የሚወድ ሰው ቢኖር

አኮኑ ያቀድም ይንበር ወየሐስብ ፃዕፃዖ ።

አስቀድሞ ተቀምጦ የሚበቃውን ያስብ የለምን ።

እመ የአክሎ ከመ ይሣርር መሠረተ ።

ይበቃው እንደሆነ መሠረት ይጀምር ዘንድ ።

፳፱ ከመ ሣሪሮ መሠረተ እመ ሰእነ ፈጽሞ ኵሎሙ እለ ርእይዎ ይእኅዙ ይሣለቁ ላዕሌሁ እንዘ ይብሉ ዝንቱ ብእሲ አኃዘ ይኅንጽ ወስዕነ ፈጽሞ ።

፳፱ መሠረት ጀምሮ መፈጸም የተሳነው እንደሆነ ያዩት ሰዎች ሁሉ ይህ ሰው ቤቱን ሊሠራ ጀምሮ ነበር መፈጸም ተሳነው ብለው እንዲዘብቱበት አንድም እመቦ ብለህ መልስ ከናንተ ወገን የምናኔ ሥራ ሊሠራ የሚወድ ሰው ቢኖር ይቻለውም አይቻለውም እንደሆነ በዓለም ሳለ ያወጣ ያወርድ የለምን ። ከመ ሣሪሮ ከጀመረ በኋላ መፈጸም ቢሳነው ያዩት ሰዎች ያዩት እጋንንት ይህ ሰው የምናኔ ሥራ ሊሠራ ጀምሮ ነበር መፈጸም ተሳነው ብለው እንዲዘብቱበት ።

፴፩ ወእመኒ ንጉሥ ፈቀደ ይሑር ይጽብኦ ለካልዕ ንጉሥ ።

፴፩ ንጉሥ ንጉሥን ሊወጋው ቢወድ ። አኮኑ ይቀድም ወይነብር ወይመክር ለእመ ይክል በእልፍ ጸቢአቶ ለዘይመጽእ ኀቤሁ ምስለ ክልኤ እልፍ፡ ሁለት እልፍ አስከትሎ የሚመጣበትን ንጉሥ እልፍ ሠራዊት ይዞ ድል ይነሣው እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ አውጥቶ አውርዶ ይመክር የለምን ።

፴፪ ወእመ አኮሰ እንዘ ርኁቅ ውእቱ ይፌኑ ተናብልተ ።

፴፪ ያለዚያ ግን በሩቅ ሳለ ልገብር ብሎ እማላጅ ይልክ የለምን ። ወይዜንውዎ ሰላመ ። ልገብር እለ ብለው ይነግሩት የለምን ። አንድም ባሕታዊ ሰይጣንን ድል ሊነሣው ቢወድ አስቀድሞ በዓለም ሳለ ያወጣ ያወርድ የለምን ለእመ ይክል ፍትወታት እኩያት ኃጣውእን የሚያመጣበት ሰይጣንን በጥቂት ትሩፋት ድል መንሣት ይቻለውም እንደሆነ ወእመ አኮሰ ያለዚያ ግን በበላዩ ወዳሉ ባሕታውያን አትርሱኝ አዘኑልኝ ብሎ ይልክ የለምን ።

፴፫ ወከማሁ ኵሉ ሰብእ ዘእምኔክሙ ዘኢወዕአ እምኵሉ ወዘኢይትናከር ኵሎ ዘዚአሁ ንዋየ ኢይክል ከዊነ ረድዕየ ። ማቴ. ፭ ፲፫ ማር. ፱ ፡ ፶ ።

፴፫ እንደዚህም ሁሉ ከናንተ ወገን ከቤቱን ሁሉ ያልተወ ከገንዘቡ ሁሉ ያልተለየ የኔ ደቀ መዝሙር መሆን አይቻለውም ።

፴፬ ሠናይ ውእቱ ጼው ።

፴፬ ጨው መልካም ነው ።

ወእመሰ ጼው ለስሐ በምንት እንከ ይቄስምዎ ።

ጨው ቢያልጥ ግን በምን ያጣፍጡታል ።

፴፭ አኮኑ ይገድፍዎ አፍአ ውስተ መሬት።

፴፭ ከዳሪ ይጥሉታል እንጂ ።

፴፮ ዘቦ እዝነ ሰሚዓ ለይስማዕ ።

፴፮ ጆሮ ያለው ይስማ አንድም ሠናይ ውእቱ ጼው ብለህ መልስ ምናኔ መልካም ነው ምናኔ ከሌለ የተባሕትዎውን ሥራ በምን ይሠሩታል ዘቦ እዝነ ጼው የተባለ በቁሙ ጨው እንዳይደለ ምናኔ እንደ ሆነ እዝነ ልቡና ያለው ያስተውል ።

በእንተ ተገድፎተ በግዕ ።

ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወቀርቡ ኀቤሁ መጸብሓን ወኃጥአን ይስ ዐምዎ ።

፩ ቀራጮች ኃጥአንም ከርሱ ሊሰሙ ወደርሱ ቀረቡ ።

፪ ወእንጐርጐሩ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን እንዘ ይብሉ ዝንቱሰ ኃጥአነ ይትዌከፍ ።

፪ ፈሪሳውያንና ጸፎችም እንጐራጐሩ እንዲህ ሲሉ ይህስ ኃጢአተኞችን ይቀበላል ።
ወይበልዕ ምስሌሆሙ ።
ከርሳቸውም ጋራ ይበላል ።

፫ ወመሰለ ሎሙ ዘንተ ምሳሌ ወከመዝ ይቤሎ።
፫ እንዲህ ያለ ምሳሌ መስሎ መስሎ ነገራቸው
፬ እመቦ ብእሲ እምኔክሙ ዘቦ ምእት አባግዕ
፬ ከናንተ ወገን መቶ አባግዕ ያሉት ቢኖር ።
ወለእመ ተገድፎ አሐዱ እምኔሆሙ ።
ከመቶው አንዱ ቢጠፋበት ።
አኮኑ የኀድግ ተሰዓ ወተሰዓተ ውስተ ገዳም ወየሐውር ይኅሥሥ ኀበ እንተ ተገድፎ ።
ዘጠና ዘጠኙን ከበረሀ ትቶ ወደጠፋበት ሊሻ ይሄድ የለምን ።
እስከ ይረክቦ ።
እስኪያገኘው ድረስ ።

፭ ወእምከመ ረከቦ ይጸውሮ ዲበ መትከፍቱ እንዘ ይትፌሣሕ ።

፭ ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በትከሻው ይሸከመው የለምን ።

፮ ወአቲዎ ቤቶ ይጼውዕ አእርክቲሁ ወጎረ ።
፮ ከቤቱም በገባ ጊዜ ጐረቤቶቹንና ወዳጆቹን ጠርቶ ፣
ወይቤሎሙ ተፈሥሑ ሊተ ፣
ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል ፤
እስመ ረከብኩ በግዕየ ዘተገድፈኒ ።
የጠፋብኝን በጌን አግኝቼዋለሁና ።

፯ እብለክሙ ከመ ከመዝ ይከውን ዓቢይ ትፍሥሕት በሰማያት በበይነ ፩ዱ ኃጥእ ዘይኔሥሕ ፈድ

ፋደ እምተስዓ ወተስዐቱ ጻድቃን እለ ኢይፈቅዱ ይነስሑ ።

፯ ንስሐን ከማይሹ ከዘጠና ዘጠኙ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ ባንድ ኃጥእ እንደዚህ ያለ ደስታ በሰማይ ይደረጋል ብየ እነግራችኋለሁ ።

በእንተ ተረክቦተ ገመስ ።

፰ ወእመኒ ብእሲት ዘባቲ ዓሥሩ ጠፋልሐ አግሙስ ።

፰ እንደዚሁም ሁሉ ዐሥር ምዝምዝ የወርቅ ቀለበት ያላት ሴት ብትኖር ።
ወለእመ ትገድፈታ አሐቲ እምኔሆን ።
ካሥሩ አንዲቱ ብትጠፋባት ።
አኮኑ ታሐቱ ማሕቶተ ወትፈነቅል ኵሎ ንዋያ ዘው ስተ ቤታ ወትኮስትር ወትነሥሥ እስተሐሚማ ።
መብራት አብርታ ቤቷን ጠርጋ ዕቃዋን አውጥታ ፣
ትግታ ትፈልገው የለምን ።
እስከ ትረክቦ ።
እስከታገኘው ድረስ ።

፱ ወእምከመ ረከበት ትጼውዕ አእርክቲሃ ወአግዋሪሃ ።

፱ ያገኘችው እንደሆነ ጐረቤቶቿን ወዳጆቿን ጠርታ ።
ወትቤሎሙ ተፈሥሑ ሊተ ።
ከኔ ጋራ ደስ ይበላችሁ ።
እስመ ረከብኩ ገመስየ እንተ ተገድፈተኒ ።
የጠፋብኝን ቀለበቴን አግኝቻታለሁና የምትላቸው አይደለምን ።

፲ እብለክሙ ከመ ከማሁ ይከውን ፍሥሐ በሰማያት በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር በእንተ ኢሐዱ ኃጥእ ዘይኔስሕ ።

፲ ንስሐ ስለሚገባ ስለ ፩ድ ኃጥእ በእግዚአብሔር መላእክት ዘንድ እንዲህ ያለ ደስታ ይደረጋል ብየ እነግራችኋለሁ ። ሐተታ ማቴዎስ መቶ አለ ። ሉቃስ ዐሥር አለ እንደምን ነው ቢሉ መቶው የኅጥ አለቃ ዐሥር ደምሳሽ አለቃ አላቸው ከመቶው የንጥ አለቃ አንዱ ዲያብሎስ ወርዷልና ። ማቴዎስ መቶ አለ ካሥሩ ደምሳሽ አለቃ አንዱ ዲያብሎስ ወርዷልና ሉቃስ እንዲህ አለ አንድም በከተማ ዐሥር በነገድ መቶ ናቸውና ካሥሩ ከተማ አንዱ ዲያብሎስ ወርዷልና ሉቃስ ዐሥር አለ ከመቶው ነገድ አንዱ ዲያብሎስ ወርዷልና መቶ አለ ።

በእንተ ተኀጕሎቱ ወተመይጦቱ ለወልድ ።

፲፩ ወይቤሎሙ ካዕበ እግዚእ ኢየሱስ አሐዱ ብእሲ ቦቱ ክልኤቱ ደቂቅ ።

፲፩ ላንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት

፲፪ ወይቤሎ ዘይንእስ ወልዱ ለአቡሁ አባ ሀበኒ መክፈልተ ርስትየ ዘይረከበኒ እምንዋይከ

፲፪ ታናሹ ልጁ አባቱን አባቴ
ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍለህ ስጠኝ አለው ።
ወከፈሎ መክፈልቶ እምንዋዩ
ገንዘቡንም ከፍሎ ሰጠው ።

፲፫ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል አስተጋብአ ኵሎ ንዋዮ ዝኩ ወልዱ ዘይንእስ ሖረ ወነገደ ርኁቀ ብሔረ ።

፲፫ ታናሽ ልጁ ከጥቂት ቀን በኋላ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደሩቅ አገር ሄደ ።
ወበህየ ዘረወ ወአማሰነ ኵሎ ንዋዮ እንዘ የሐዩ በምርዓት በዚያም አገር በድርዓት እየኖረ ገንዘቡን ሁሉ አበላሸ ።

፲፬ ወአኅሊቆ ኵሎ ንዋዮ መጽአ ረኃብ ዓቢይ ውስተ ውእቱ ብሔር ።

፲፬ በድርዓት እየኖረ ገንዘቡን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ በዚያ አገር ጽኑ ረኃብ ሆነ ።
ወተፀነሰ ፡ ተቸገረ ።

፲፭ ወሖረ ወተፀምደ ኀበ አሐዱ እምሰብእ ውእቱ ብሔር ።

፲፭ ሄዶም በዚያ አገር ካሉ ሰዎች ላንዱ ተገዥ ሆነ ።
ወፈነዎ ውስተ ዓጸደ ወፍሩ ይርአይ አኅርወ ።
እርያ ይጠብቅ ዘንድ እርሱ ወደሚሠማራበት አስ ማራው ።

፲፮ ወፈተወ ይጽገብ እምሐመረ ጽራዕ ዘይሴሰዩ አኅርው ።

፲፮ እሪያዎች የሚመገቡትን ተረን ቃሞ ሊመገብ ወደደ ።
ወአልቦ ዘይሁቦ
ያኑ ቅሉ የሚሰጠው የለም አለ እሪያዎች እየተቀደሙ እየበሉበት አንድም በቃህ የሚለው አጣ ።
አንድም እህል የሚሰጠው አላገኘም ።

፲፯ ወሐለየ በልቡ ወይቤ ሚመጠን አግብርቲሁ ለአቡየ እለ ያተርፍዎ ለእክል ።

፲፯ በልቡ አስቦ በቃሉ እንዲህ አለ ባባቴ ቤት እህል ተርፏቸው የሚኖሩ ያባቴ ቤተሰዎች ምን ያህላሉ ።
ወአንሰ እመውት በረኃብ በዝየ ።
እኔ ግን እህል አጥቼ በባዕድ አገር በረኃብ እሞታለሁ ።

፲፰ አትንሣእ ወእሐውር ኀበ አቡየ ።
፲፰ ተነሥቼ ወደ አባቴ እሄዳለሁ
ወእብሎ አባ አበስኩ በሰማይኒ ወበቅድሜከኒ ።
አባቴ አንተንም ፈጣሪዬንም በደልኩ ።

፲፱ ወኢይደልወኒ እንከ እሰመይ ወልደከ ።
፲፱ እንግዲህ ወዲህ ልጅህ ልባል አይገባኝም
አላ ረስየኒ ከመ አሐዱ እምአግብርቲከ ።
ከባሮችህ እንዳንዱ ቍጠረኝ እንጂ እለዋለሁ ብሎ።

፳ ወተንሥአ ወሖረ ኀበ አቡሁ ።
፳ ተነሥቶም ወደአባቱ ሄደ ።
ወርእዮ አቡሁ እምርኁቅ ምሕሮ ።
እባቱም በሩቅ አይቶ አዘነለት ።
ወሮጸ ወሐቀፎ ከማዶ ወሰዓሞ ።
ፈጥኖ አንገቱን አቅፎ ሳመው

፳፩ ወይቤሎ ወልዱ ለአቡሁ አባ አበስኩ በሰማይኒ ወበቅድሜከኒ ።

፳፩ ልጁም አለ አባቴ አንተንም ፈጣሪዬንም በደልኩ ።
ወኢይደልወኒ እንከ እሰመይ ወልደከ ።
ከእንግዲህ ወዲህ ልጅህ ልባል አይገባኝም ።
አላ ረስየኒ ከመ አሐዱ እምአግብርቲከ ።
ከባሮችህ እንዳንዱ ቍጠረኝ እንጂ አለው ።

፳፪ ወይቤሎሙ አቡሁ ለአግብርቲሁ አምጽኡ ፍጡነ እልባሰ ቀድመ ወአልብስዎ ።

፳፪ አባቱ ባሮቹን አለ ያማረውን ግምጃ ቶሎ ጥታችሁ ፈጥናችሁ አልብሱት ።
ወደዩ ሕልቀተ ውስተ አፃብዒሁ ወአሣዕነ ውስተ እገሪሁ ።
ቀለበት ከጣቱ ጫማ ከእግሩ አግቡለት አላቸው ።

፳፫ ወአምጽኡ ላሕመ መግዝዓ ወጥብሑ ።
፳፫ ማለፊያ ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱ ።
ንብላዕ ወንትፈሣሕ ምስሌሁ ።
በልተን ከሱ ጋራ ደስ ይበለን

፳፬ እስመ ዝንቱ ወልድየ ሞተኒ ወሐይወ ።
፳፬ ይህ ልጄ ሞተ ካልሁት በኋላ ደኑዋልና ።
ተኀጕለኒ ወተረክበ ።
ጠፋ ካልሁት በኋላ ተገኝቷልና ።
ወአኀዙ ይትፈሥሑ ።
ተድላ ደስታ ያደርጉ ጀመሩ ።

፳፭ ወወልዱሰ ዘይልሕቅ ሀሎ ውስተ ሐቅል ።
፳፭ ታላቁ ልጁ ግን ከበረሀ ነበር ።
ወሶበ በጽሐ ወቀርበ ኀበ ጸንፈ ሀገር ።
ተመልሶ ከከተማ ሊገባ በቀረበ ጊዜ ።
ሰምዓ ዕንዚራ ወማኅሌተ ።
የዘፈን የጫወታ ድምፅ ሰማ ።

፳፮ ወጸውዓ አሐደ እምአግብርተ አቡሁ ወይቤሎ ምንትኑ ዝ ዘእሰምዕ ።

፳፮ ካባቱ ባሮች አንዱን ጠርቶ ይህ የምሰማው ምንድርነው አለው ።

፳፯ ወይቤሎ እስመ አተወ እኁከ ወጠብሐ አቡከ ላህመ መግዝዓ ።

፳፯ ወንድምህ መጥቷልና አባትህ ሜልኅች አርዶለታል ።
እስመ ረከቦ ሕያዎ ።
ሞቶ ካለው በኋላ ደኑዋል ጠፋ ካለው በኋላ ተገኝቷልና አለው ።
፳፰ ወተምዓ ወአበየ በዊአ ።
፳፰ ተቆጥቶ አልገባም አለ ።
ወወፅአ አቡሁ ወአስተብቍዖ ።
አባቱም ወጥቶ ማለደው ።

፳፱ ወአውሥአ ወይቤሎ ናሁ መጠነ ዝ ዓመታተ ተቀነይኩ ለከ ።

፳፱ እነሆ ይህን ያህል ዘመን ተገዛሁልህ ።
ወኢኃለፍኩ ወኢተዓደውኩ እምትእዛዝከ ግሙራ ።
ከቶ ከትእዛዝህ አልወጣሁም ትእዛዝህን አላፈረስኩም
ወሊተሰ ኢወሀብከኒ መሐስአ ጠሊ ጥቀ በዘእትፌሣሕ ቦቱ ምስለ አዕርክትየ ወአብያጽየ ።
ለኔ ግን ከባልንጀሮቼ ከወዳጆቼ ጋራ ደስ በሚለኝ ገንዘብ ደስ ይለኝ ዘንድ የፍየል ጠቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም ።

፴ ወአቲዎሰ ዝንቱ ወልድከ ዘአኅለቀ ኵሎ ንዋየከ ምስለ ዘማት ጠባሕከ ሎቱ ላህመ መግዝዓ ።

፴ በድርአት እየኖረ ገንዘብህን ያበላሸ ይህ ልጅህ በተመለሰ ጊዜ ግን ሜልኅች አረድክለት ።

፴፩ ወይቤሎ አቡሁ ወልድየ አንተሰ ዓ ዘልፈ ሀሎከ ምስሌየ ።

፴፩ እባቱም አለው ልጄ አንተስ ዘወትር ከኔ ጋራ ትኖራለህ ።
ወኵሉ ዘዚእየ ዚአከ ውእቱ ።
የእኔም ገንዘብ ሁሉ ገንዘብህ ነው ።

፴፪ ወባሕቱ ርቱዕሰ ንትፈሣሕ ።
፴፪ አገባብስ በዚህ ደስ ሊለን ይገባል ።
እስመ ዝንቱ እኁከ ሞተኒ ወሐይወ ተኀጕለኒ ወተረክበ ።

ይህ ልጄ ከሞተ በኋላ ድንዋል ከጠፋም በኋላ ተገኝቷልና አንድም አሐዱ ብእሲ አያልከ መልስ ። ብእሲ የተባለ ጌታ ነው እንደ ታላቅ ልጅ ጸሐፍት ፈሪሳውያን እንደ ታናሽ ልጅ ኃጥአን መጸብሐን ናቸው ። አባ ህበኒ መክፈልተ ርስትየ ።

ለሁሉም እንዲያሻቸው ዐውቆ ሕግ መሥራቱን መናገር ነው ።

ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል ። ኃጥአን መጸብሐን ሕጉን ተቀብለው ጥቂት ቀን ከኖሩ በኋላ ወደ አሕዛብ ሀገር ሄዱ ። ወበህየ ዘረወ በአምልኮተ ጣዖት በገቢረ ኃጢአት እየኖሩ ሕጉን አፈረሱ ። ወአኅሊቆ ሕጉን ካፈረሱ በኋላ ። መጽአ ረኃብ ዓቢይ የሚያስተምራቸው አጡ ። ወተፀነሱ ከትምህርት ተቸገሩ ወሖረ ወተጸምደ በዚያ ሀገር ካሉ ሰዎች ለአንዱ ተገዢ ሆኑ ። ወፈነዎ ውስተ ዓጸደ ወፍሩ ይርአይ አኅርወ ። አሕዛብን ይመስሉ ዘንድ ወደሚሠሩት ኃጢአት ወደሚያመልኩት ጣዖት አሠማሯቸው ። ወፈነወ ይጸገብ የሚሠሩትን ኃጢአት ሊሠሩ የሚያመልኩትን ጣዖትሊያመልኩ ወደዱ ሠሩ አመለኩ። ወአልቦ የሚያስተምራቸው አጡ ። በልቡናቸው አሰበው እንዲህ አሉ ባባታችን ቤት በቤተ መቅደስ እህል ትምህርት ተርፏቸው የሚኖሩ ምእመናን ምን ያህላሉ ። ወአንሰ አመውት ። እኛ ግን በአሕዛብ አገር የሚያስተምረን አጥተን በነፍስ እንሞታለን ። እትነሣእ ወእሐውር ። ንስሐ ገብተን ወደ አባታችን ወደ እግዛአብሔር ተመልሰን ወእብሎ መለኮትህን ትስብእትህን በደልን ወኢይደልወኒ ከእንግዲህወዲህ ወልድየ ዘበኵርየ ከተባሉ ከእስራኤል ልንቈጠር አይገባንም ። አላ ከመ አሐዱ ከተነሣሕያን አሕዛብ አንዳንዱ ቍጠረን እንጂ እንለዋለን ብለው ሄዱ ። ወርእዮ አቡሁ አላበጀንም ማለታቸውን አውቆ አዘነላቸው ወሮጸ ፈጥኖ በረድኤት ተቀበላቸው ።

ወሰዓሞ በፍቅር ወደዳቸው ወይቤሎ ወልዱ መለኮትህን ትስብእትህን በደልን ወኢይደልወኒ ። ከእንግዲህ ወዲህ ወልድየ ዘበኵርየ ከተባሉ ከእስራኤል ልንቈጠር አይገባንም ። አላ ረስየኒ ከተነሣሕያን አሕዛብ እንዳንዱ ቍጠረን እንጂ አሉት ወይቤሎ አቡሁ ። ጌታ ሐዋርያትን አልባስ ቅድወ ልጅነት እንዲሰጣቸው ወደዩ ኅልቀተ ሃይማኖትን እንዲይዙ ወአሣዕነ ምግባር እንዲሠሩ አድርጓቸው አላቸው ።

ወአምጽኡ ላህመ ታምራት አድርጉላቸው እስመ ዝኩ ወልድየ ኃጥአን መጸብሐን ከሞቱ በኋላ ድነዋል ከጠፉ በኋላ ተገኝተዋልና ። ወአኃዙ ይትፈሥሑ በትምህርት ተድላ ደስታ ያደርጉ ጀመር ወወልዱስ ፈሪሳውያን ግን እሪትን እንጠብቃለን ይሉ ነበር ወአቲዎ ። በወንጌል እናምናለን ብለው ባሉ ጊዜ ሰምዓ እንዚራ ለኃጥአን መጸብሐን የተደረገውን ታምራት ሰሙ ወጸውዓ አሐደ ፤ አንዱ እንዱን ጠርቶ ይህ የምሰማው ምንድርነው አለው ። ወይቤሎ እስመ አተወ ። ኃጥአን መጸብሐን በወንጌል ሰላሙ ። ወጠብሐ ። ደጋጉን ጠቃቅኑን ተአምራት አድርጎላቸዋል ። እስመ አተወ ከሞቱ በኋላ ድነዋል ። ከጠፉ በኋላ ተገኝተዋልና አለው ።

ወተምዓ ወአበየ ዝሰ ኃጥአነ ይትዌከፍ ኅበ ብእሲ ኃጥእ ቦአ ያለማለታቸውን መናገር ነው ። ወመጽአ አቡሁ ወአኮ ጥዑያን ማለቱን መናገር ነው ። ናሁ መጠነዝ ይህን ያህል ዓመት ባሥሩ ቃላት ጸንተን ተገዛንልህ ወኢኃለፍኩ ዓሠርቱ ቃላትን አላፈረስንም ። ወሊተሰ ለኛ ግን ከባልንጀሮቻችን ጋራ ደስ በሚለን ገንዘብ ጥቂት ስንኳ ተአምራት አላደረግህልንም ወአቲዎሰ በአምልኮተ ጣዖት በገቢረ ኃጢአት እየኖሩ ሕግን ያፈረሱ ኃጥአን መጸብሐን በተመለሱ ጊዜ ግን ደጋጉን ጠቃቅኑን ተአምራት አደረግህላቸው ።

ወልድየ አንተሰ ሀሎከ ምስሌየ ወኵሉ ዚአየ ኢመጽአኩ እጸውዕ ጻድቃነ ማለቱን መናገር ነው ወባሕቱ ርቱዕሰ ሕሙማን ይፈቅድዎ ለዓቃቤ ስራይ አላ ኃጥአን ለንስሐ ማለቱን መናገር ነው ። አንድም አሐዱ ብእሲ ብለህ መልስ ከልኤቱ ደቂቅ የተባሉ እንደ ታላቅ ልጅ ባሕታውያን እንደ ታናሽ ልጅ ሰብአ ዓለም ናቸው ወይቤሎ ዘይንእስ ለሁሉም ሕግ እንዲያሻቸው አውቆ ሕግ መሥራቱን መናገር ነው ወእምድኅረ ኅዳጥ ። ሰብአ ዓለም ሕጉን ተቀብለው ጥቂት ቀን ከኖሩ በኋላ ወደ አሕዛብ አገር ሄዱ ። ወበህየ ዘረወ በኃጢአት እየኖሩ ሕጉን አፈረሱ ወአኅሊቆ ብለህ ወኢይደልወኒ እስካለው ጣዖትን ብቻ እየተውክ አውርድ ወኢይደልወኒ። ከእንግዲህ ወዲህ በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን ከተባሉት ልንቈጠር አይገባንም አላ ረስየኒ ከተነሳሕያን አሕዛብ ቍጠረን እንጂ እንለዋለን ብለው ሄዱ ።

ወርእዮ አቡሁ እንዳለፈው ወአምጽኡ አልባስ ቅድወ ልጅነት እንዲመለሰላቸው ወደዩ ኅልቀተ ሃይማኖትን እንዲረዱ ምግባር እንዲሠሩ አድርጉላቸው ወአምጽኡ ላህመ ሥጋውን ደሙን ስጧቸው ንብላዕ በልተን ደስ ይበለን እስመ ዝንቱ ወልድየ ሰብአ ዓለም ከጠፉ በኋላ ተገኝተዋል ከሞቱ በኋላ ድነዋልና ወአኃዙ በነፍስ ተድላ ደስታ ያደርጉ ጀመር ወወልዱሰ ዘይልሕቅ ባሕታውያን ግን በበረሀ ነበሩ ወአቲዎ ወደዓለም በመረመሩ ጊዜ ሰምዓ ዕንዚራ ለሰብአ ዓለም የተደረገውን ሰሙ ወጸውዓ ወይቤሎ አንዱ አንዱን ጠርቶ ይህ የምንሰማው ምንድርነው ብሎ ጠየቀው ። ወይቤሎ እስመ አተወ ሰብአ ዓለም ከጠፉ በኋላ ተገኝተዋል ከሞቱ በኋላ ድነዋል ።

ወጠብሐ ሎቱ ሥጋውን ደሙን ስጥቷቸዋልና እስመ ረከበ ከጠፉ በኋላ ተገኝተዋል ከሞቱ በኋላ ድነዋልና ። ወተሞዓ ቁጣ የለም አደነቁ ። ወአበየ በዊአ በዚያው ጸኑ ወመጽአ አቡሁ ጌታቸው በዚያው አጸናቸው ወአውሥአ ወይቤሎ ይህን ያህል ዘመን በተባሕትዎ ጸንተን ተገዝንልህ ወኢኃለፍኩ ዐሠርቱ ቃላትን አላፈረስንም ወሊተሰ ለኛ ግን ጥቂት ስንኳ ተአምራት አላደረግህልንም ወኢቲዎ በኃጢአት እየኖሩ ሕግህን ያፈረሱ ሰብአ ዓለም በተመለሱ ጊዜ ግን ሥጋህን ደምህን ሰጠሀቸው አሉት ። ወይቤሎ አቡሁ በናንተስ አድሬባችሁ እኖራለሁ ወኵሉ ዚአየ ተአምራቱንም እናንተው ታደርጉታላችሁ እንባብስ በሰብአ ዓለም ደስ ሊለን ይገባል ።

እስመ ዝንቱ ሰብአ ዓለም ከጠፉ በኋላ ተገኝተዋል ከሞቱ በኋላ ድነዋልና እንድም አሐዱ ብእሲ ብለህ መልስ ክልኤቱ ደቂቅ የተባሉ መላእክትና ደቂቀ አዳም ናቸው እንደ ታላቅ ልጅ መላእክት እንደ ታናሽ ልጅ ደቂቀ አዳም ናቸው ። አስተሐምሞተ አኃው ዓቢያን ከመ ዘለንኡሳን እንዲል ወይቤሎ ወልዱ ለሁሉም እንዲያሻቸው አውቆ ሕግ መሥራቱን መናገር ነው ትርጓሜው አይለወጥም

ምዕራፍ ፲፮ ።

በእንተ መጋቢ ዘኢይትአመን ።

፩ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ፩ዱ ብእሲ ባዕል ቦቱ መጋቢ ወከመዝ ኮነ መጋቢሁ ዘያማስን ንዋዮ ።

፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው ላንድ ባለጸጋ ገንዘቡን የሚያበላሽ አንድ ሹም ነበረው ።
ወአስተዋደይዎ ኀቤሁ ከመ ይዘሩ ኵሎ ንዋዮ ።
ገንዘብህን ሁሉ ያበላሻል ብለው ከሰሱት ።

፪ ወጸውዖ እግዚኡ ወይቤሎ ምንትኑዝ ዘእሰምዕ በእንቲአከ ፧

፪ ጌታው ጠርቶ ይህ የምሰማብህ ነገር ምን ድር ነው አለው ።
አግብእ እንከሰ ሐሳበ ምግብናከ ።
እንግዲህስ ወዲህ ሹመትህን አበርክተኝ ።
እስመ ኢትክውነኒ እንከ መጋቤ ሊተ ።
ከእንግዲህ ወዲህ ሹም አትሆነኝምና አለው ።

፫ ወሐለየ ውእቱ መጋቢ ።
፫ ያም ሹም አሰበ ።
ወይቤ ምንተ እሬሲ ።
ምን ላድርግ አለ ።
ናሁ ይሥዕረኒ እግዚእየ እምግብናየ ።
እነሆ ጌታዬ ከሹመቴ ይሽረኛል ።
ሐሪሰኒ ኢይክል ።
እርሻ አልችል ።
ወሰኢለኒ አኃፍር ።
እንዳለምንም አፍራለሁ ።

፬ አአምር እንከሰ ዘእገብር ።
፬ እንግዲህስ ወዲህ የማደርገውን አውቃለሁ
እምከመ ሠዓረኒ እግዚእየ እምግብናየ ።
ጌታዬ ከሹመቴ የሻረኝ እንደሆነ ።
ከመ ይትወከፉኒ ውስተ አብያቲሆሙ ።
በቤታቸው ይቀበሉኝ ዘንድ ብሎ ።

፭ ወጸውዖሙ ለእለ ይፈድይዎ ዕዳ ለእግዚኡ ።
፭ የጌታውን ባለዕዳዎች ጠርቶ
ወይቤሎ ለቀዳማዊ ሚመጠነ ዕዳ ትፈድዮ ለእግዚእየ ።
አንዱን አንተ ለጌታዬ ምን ያህል ትከፍለዋለህ አለው ።
ወይቤሎ ፻ቱ በመሥፈርቱ ባዶስ ቅብዓ ።
መቶ ማድጋ ዘይት ነው አለው እንድም ዘትፈድዮ የምትከፍለው ምን ያህል ነው አለው መቶ ማድጋ ዘይት አለብኝ አለው ።
ወይቤሎ ናሁኬ መጽሐፍከ ።
እነሆ ደብዳቤህ ።
ንበር ወጸሐፍ ፍጡነ ሃምሳ ላዕሌከ ።
ሃምሳ ነው ብለህ ፈጥነህ ጻፍ ሃምሳው ይቅርልህ አለው ።

፯ ወይቤሎ ለካልኡ አንተሰ ሚመጠነ ዕዳ ትፈድዮ ለእግዚእየ ።

፯ ሌላውንም አንተስ ለጌታዬ ምን ያህል ትከፍለዋለህ ። ዘትፈድዮ የምትከፍለው ምን ያህል ነው አለው ።
ወይቤሎ ምእተ በመሥፈርተ ቆሮስ ሥርናየ ።
መቶ ቆሮስ ሥንዴ አለብኝ አለው ሐተታ አንዱ ቆሮስ ያሥራ ሁለት በቅሎ ጭነት የሚያነሣ ዐሥራ ሁለት ጫን ነው ።

፯ ወይቤሎ ናሁኬ መጽሐፍከ ።
፯ እነሆ ደብዳቤህ ።
ንበር ወጸሐፍ ፍጡነ ሰማንያ ላዕሌከ ።
ሰማንያ ነው ብለህ ፈጥነህ ጻፍ ሃያው ይቅርልህ አለው ።

፰ ወንዕዶ እግዚአብሔር ለመጋቤ ዓመፃ ።
፰ እግዚአብሔርም ይህን የግፍ ሹም አመሰገነው ።
እስመ ከመ ጠቢብ ገብረ ያዋቂ ሥራ ሠርቷልና ።
እስመ ውሉደ ዝዓለም ይጠበቡ እምውሉደ ብርሃን በዓለሞሙ ።
ከብርሃን ልጆች ከጻድቃን ይልቅ የዚህ ዓለም ልጆች በዓለማቸው የሚራቀቁ ስለሆኑ ሐተታ እኒያ ይህን ዓለም በወዲያው ዓለም ለውጠው ይገባሉ እኒህ

ግን በወዲሁም ሰጥተው መጽውተው በወዲያውም ደስ ይላቸዋልና አንድም አሐዱ ብእሲ እያልክ መልሰ ባዕል የተባለ ጌታ ነው ። ለጌታ ባለጸጋ ሹም አለው ጌታ ሰውን ባለጸጋ ማድረጉ በድኆች ላይ መሾሙ ነውና ። ወእስተዋደይዎ ካዝማሪ ከዘዋሪ ጋራ እየበላ አይሰጥም አይመጸውትም ብለው ነዳያን ከሰሱት ወጸውዖ ወይቤሎ ፡ ጌታም በደዌ ጠርቶ ይህ የምሰማብህ ምንድነው አግብእ እንከ ሐሳበ ምግብናከ ። ሹመትህን አበርክተኝ ። እስመ ኢትክውነኒ እንግዲህ ሹም አትሆነኝምና አለው ። ወሐለየ እንግዴሁ ምን ሳድርግ ፤ ናሁ ይሥዕረኒ ፡ እነሆ ጌታዬ ነፍሴን ከሥጋዬ ይለያታል ሐሪሰኒ ገሃነም ክገቡ በኋላ ሃይማኖት ይዞ ምግባር ሠርቶ ክብር ማግኘት መንግሥተ ሰማያት መግባት አይቻልም ።

አአምር እንግዲህስ ወዲህ የምሠራውን አውቃለሁ ። እምከመ ሠዐረኒ ጌታዬ ነፍሴን ከሥጋዬ የለያት እንደሆነ ከመ ይትወከፉኒ ነዳያን በቤታቸው በመንግሥተ ሰማይ ይቀበሉኝ ዘንድ በርሳቸው ምክንያት የምትወረስ ስለሆነች አብያቲሆሙ አለ ። ዕድው ድኩማን የሐንጸ አብያተ እንዲል ። ወጸውዖሙ ኃጢአት ሠርተው ፍዳ የሚቀበሉትን ጠርቶ ወይቤሎ ለቀዳማዊ አንዱን ምን ቸግሮሃል አለሁ ምግብ አለኝ ልብስ የለኝም ልብስ አለኝ ምግብ የለኝም አለው ። ወይቤሎ ናሁኬ የቸገረህን ውሰድ አለው ። ወይቤሎ ለካልዑሂ ሌላውንም አንተስ ምን ቸግሮሃል የቸገረህ ምንድርነው አለው ልብስ ምግብ አለኝ ከልብስ ከምግብ ቀሚስ ሰናፊል ቸግሮኛል አለው ። ወይቤሎ ናሁኬ የቸገረህን ውሰድ አለው ። ወንዕዶ እግዚአብሔር በኃላፊ ክብት የተሾመ ባለጸጋን እግዚአብሔር አመሰገነው እስመ ከመ ጠቢብ ገብረ ያዋቂ ሥራ ሠርቷልና ። እስመ ውሉደ ዝዓለም ይጠበቡ እምውሉደ ብርሃን በዓለሞሙ ከውሉደ ብርሃን ከጻድቃን ይልቅ ሰብአ ዓለም በዓለማቸው የሚራቀቁ ስለ ሆነ ። ሐተታ ጻድቃን በዚህ ዓለም የወዲያኛውን ዓለም ለውጠው ይገባሉ እሊህ ግን ይህ ሳይቀርባቸው መጥተው ዐሥራት በኵራት አውጥተው ያን ዓለም ይወርሱታልና ታሪክ እንደ ፩ድ ንጉሥ ያንድ አገር ሰዎች ዓመት አንግሠው ከደሴት ያግዙታል በረኃብ በጽም ይሞታል አንድ ንጉሥ ግን ይህን ያውቃልና ከነገሠባት ቀን ጀምሮ ገንዘብ እየሰደደ ሲያከማች ኖረ እንደ ልማዳቸው አጋዙት ያኖረውን እየተመገበ በተድላ የሚኖር ሆኑዋል እንደ ዚህም ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሰጡ ቢመጸውቱ በወዲያኛው ክብር ይገኛል ። አንድም አሐዱ ብእሲ ብለህ መልስ ብእሲ አይለወጥም ለጌታ ሹም አለው መምህረ ንስሐ ነው አያስተምርም ንስሐን ሥጋውን ደሙን አይሰጥም ብለው ምእመናን ከሰሱት ወጸውዖ ጌታ በደዌ ጸራው ከዚህ በላይ አይለወጥም ወጸውዖሙ ። ኃጢአት ሠርተው ንስሐ የሚቀበሉትን ጸራቸው ወይቤሎ ለቀዳማዊ አንተ ምን ኃጢአት ሠርተሃል የሠራኸው ኃጢአት ምንድነው አለው ። ወይቤሎ ምእተ በመሥፈርተ ባዶስ ፡ ፍጹም ኃጢአት ሠርቻለሁ አለው ወይቤሎ ጸሐፍ ላዕሌከ ሃምሳ እኩሉን ጹም እኩሉን እኔ እጸምልሃለሁ አለው ። ወይቤሎ ለካልዑ አንተስ ምን ኃጢአት ሠርተሃል አለው ወይቤሎ ምእተ ። ፍጹም ኃጢአት ሠርቻለሁ የሠራሁት ኃጢአት ፍጹም ነው አለው ። ሦስቱን እጅ አንተ ጹም ቢሶውን እኔ እጸማለሁ አለው ፤ ተመየጥ አንተ ወእነ እትዌከፍ ሞተ ህየንቴከ በከመ ተወክፈ ክርስቶስ ህየንቴየ ወህየንተ ኵሎሙ እንዲል ወንዕዶ እግዚአብሔር በዓመፃ የሚፈርድ መምህረ ንስሐን እግዚአብሔር አመሰገነው እስመ ጠቢብ ። ዐዋቂ እንደ መሆኑ ያዋቂ ሥራ ሠርቷልና እስመ ውሉደ ዝዓለም ። ከውሉደ ብርሃን ከጻድቃን ይልቅ ሰብአ ዓለም በዓለማቸው የሚራቀቁ ስለ ሆኑ ። ሐተታ ጻድቃን ራሳቸውን ጠብቀው ብቻቸውን ነው መንግሥተ ሰማይ የሚገቡ መምህራን ግን ብዙ አስተምረው አሳምነው አጥምቀው ወደኃጢአት ወደክህደት የሄደውን በንስሐ መልሰው ብዙ ሁነው ነውና ።

፱ ወአነሂ እብለክሙ ግበሩ ለክሙ አዕርክተ እምንዋየ ዓመፃ ።

፱ በኃላፊ ክብት ወዳጅ ግዙበት አላችኋለሁ ከመ አመ የሐልቅ ንዋይክሙ ይትወከፉክሙ እሙንቱሂ ውስተ አብያቲሆሙ ዘለዓለም ። ዘለዓለም ገንዘባችሁን ሰጥታችሁ በጨረሳችሁ ጊዜ እርሳቸውም በቤታቸው በመንግሥተ ሰማይ ይቀበሏችሁ ዘንድ ታሪክ እንዳንድ ባለጸጋ ፡ ክብሮ የነበረ ተዋርዶ አግኝቶ የነበረ አጥቶ ሳለ ንጉሥ አጸራው ፡ ክብሬ የነበረ ተዋርጄ አግኝቼ የነበረ አጥቼ ልብስ ስንቅ የምሰጥው ገጸ በረከት የለኝ ምን አደርጋለሁ አለ ። ከራሱ አብልጦ የሚወደው እንደ ራሱ አድርጎ የሚወደው ንቆ አጥቅቶ የሚወደው ወዳጆች ነበሩት ከራሱ አብልጦ ከሚወደው ወዳጁ ዘንድ ሂዶ አንድ ግርባብ ሰጥቶ ሰደደው እንደራሱ አድርጎ ከሚወደው ቢሄድ አልቅሶ ሸኝቶ ሰደደው ንቆ አጥቅቶ ከሚወደው ወዳጁ ዘንድ ሂዶ ምንስ ንቄ አጥቅቼ ብወደው ወዳጄ አይደለምን አንድ ነገር ቢሰጠኝ ብሎ ነገረው እርሱም አለው ሁሉ ከኔ አለልህ ልብስ ብትል ስንቅ ገጸ በረከት ብትል ውሰድ እንዲህም አድርጌ እኔ አልቀርም ከንጉሡ ባለሟል ነኝ ባለሟሎቹም ወዳጆቼ ናቸው ሂጀ ነገርህን አቀናልሃለሁ ብሎ ሂዶ ነገሩን አቅንቶለታል። ባለጸጋ የተባለ ሰው ሁሉ ነው ንጉሥ የጌታ ምሳሌ እንደማስጠራቱ ጌታ ሰውን በሞት መጥራቱን መናገር ነው ። ከራሱ

አብልጦ የሚወደው ወዳጅ የተባለ ገንዘብ ነው ። እርሱ ከጦርነት ሲሄድ ገንዘቡን ከንዳም አግቡቶት ይሄዳልና ። ገርባብ እንደሰጠው የከፈን ያህል ይዞ ይሄዳልና እንደራሱ አድርጎ የሚወደው ወዳጅ የተባለ ሚስትና ልጅ ናቸው ። አልቅሶ ሸኝቶ እንደሰደደው አልቅሰው ወደመቃብር ሸኝተውት ይመለሳሉና ። ንቆ አጥቅቶ የሚወደው ወዳጅ የተባለ ምጽዋት ነው የሚያወርሰው ክብር አልታየምና ፣ የሚሻውን ሁሉ እንደሰጠው በምጽዋት ዋጋ መገኘቱን መናገር ነው ። ለባለሟሎቹ እንደነገረለት ምጽዋት በጻድቃን በሰማዕታት በመላእክት ስም ይደረጋልና ለንጉሡ እንደነገረለት ፍጻሜው በጌታ ነውና

፲ መዘሰ በወኅድ ምእመን በብዙኅኒ ምእመን ውእቱ ።

፲ በጥቂቱ የታመነ በብዙ የታመነ ይሆናልና። መዘሰ በኅዳጥ ዓማፂ በብዙኅኒ ዓማፂ ውእቱ ።

በጥቂቱ ግን ያልታመነ በብዙውም ያልታመነ ነው ።

፲፩ ወሶበ በንዋየ ዓመፃ ሃይማኖት አልብ ከሙ በንዋየ ጽድቅ መኑ የአምነክሙ ።

፲፩ በሐሰት ከብት ካልታመናችሁ በውነተኛው ከብት ማን ያምናችኋል ማለት በሚያልፈው ገንዘብ ካልታመናችሁ የማያልፈውን ማን ይሰጣችኋል [illegible] ጽድቀ [illegible] ።

፲፪ [illegible] ሃይማኖት አልብክሙ ዘዚአክሙ መኑ ይሁበክሙ ።

፲፪ በሌላው ከብት ካልታመናችሁ ገንዘቡን አምና ማን ይሰጣችኋል ። ሐተታ እሱ ከሞተ በኋላ ልጅ ሚስት ቢበሉት ቢጠጡት ቢለብሱት ባዕድ ነውና እንድም ካልሰጠለት ለዘራፊ ለገፋፊ ይሰጥበታልና ለዝንቱስ ዘይወስድዎ ሰረቅት ወፈያት እንዲል ።

፲፫ አልቦ ገብር ዘይክል ተቀንዮ ለ፪ቱ አጋዕዝት ማቴ ፮ ፡ ፳፬ ።

፲፫ ለሁለት ጌታ መገዛት የሚቻለው ባሪያ የለም ።
ወእመ አኮ ፩ደ ያፈቅር ወካልኦ ይጸልዕ ።
ይህ ቢሆን ግን አንዱን ይወዳል አንዱንም ይጠላል። ወእመ አኮ ለአሐዱ ይትኤዘዝ ወለካልኡ የዓቢ ። ይህም ባይሆን ላንዱ ይታዘዛል ለሁለተኛውም አይታዘዝም ኢትክሉኑ ለእግዚአብሔር ተቀንዮ እንዘ ንዋየ ታፈቅሩ ገንዘብ ስትወዱ ከተገኛችሁ ገንዘብ ከወደዳችሁ ለእግዚአብሔር መገዛት አይቻላችሁም።

በእንተ ተመድልዎት ዘፈሪሳውያን ።

፲፬ ወሰሚዖሙ ዘንተ ኵሎ ፈሪሳውያን ተቃጸብዎ ።

፲፬ ፈሪሳውያን ይህን ሰምተው ተጠቃቀሱበት።

እስመ መፍቀርያነ ንዋይ እሙንቱ ።

ገንዘብ ወዳዶች ናቸውና ዛሬስ ከብት አትግዙ የሚለን መጣ ብለው ።

፲፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አንትሙሰ ትጼድቁ ለዓይነ ሰብእ ።

፲፭ እናንተስ በሰው ዘንድ ደጋግ መስላችሁ ትታያላችሁ ።

ወእግዚአብሔር የአምር ልበክሙ ።
እግዚአብሔር ግን የልባችሁን ክፋት ያውቅባችኋል። እስመ ዘበኀበ ሰብእ ዓቢይ በኀበ እግዚአብሔር ትሑት ውእቱ ።

በሰው ዘንድ የከበረው በእግዚአብሔር ዘንድ የተዋረደ ነውና ፣ ታሪክ አንድ ንጉሥ ሁለት ልጆች ነበሩት በሚሞትበት ጊዜ ታናሹን እንግሡ ብሎ ሞተ አድልቶ አይደለም ብልህ ነው ሰው ማሳደር ያውቃል ብሎ ነው እንጂ ከዕለታት ባንድ ቀን በፈረስ በሠረገላ ሁኖ ሲሄድ ታላቅ ወንድሙ ተከትሎት ሄደ ከመንገድ ቁረንጮ የለበሰ ባሕታዊ አገኘ ከፈረስ ከሠረገላ ወርዶ ከእግሩ ወድቆ እቡን ዘበሰማያት ተቀበለው ።

ታያላችሁን ይህ መንግሥት አዋራጅ ከፈረስ ከሰረገላ ወርዶ ከቁረንጮ ሲወድቅ አለው ። ሰምቶ ዝም ብሎ ሄደ ከተግባሩ ደርሶ ሲመለስ ከደጁ ነጋሪት ምቱ እሳት አንድዱ አለ በሀገራቸው ትእምርተ ጸብእ ነው እሳት እነደዱ ነጋሪት መቱ ፣ ምን አደረግሁ ምን አልከኑ ተጣላኸኝ አለው ምነው እንዲህ አላልከኝም አለው ። ቢከፋኝ እኔ መንግሥት የተዋረደ መስሎኝ ነው እንጂ አለ ፣ ከዚህ በኋላ ባረጀ ሳጥን ዝግግ ወርቅ መልቶ በባሕር ቍልፍ ቆልፎ የባሕር ዓረብ በተሸፈነ ባዲስ ሣጥን ጠጠር ገል መልቶ በባሕር ቍልፍ ቆልፎ ሁለቱንም አቅርቦ አስጠራው በል ከዚህ የመረጥኸውን ውሰድ አለው ፣ በባሕር ዓረብ የተሸፈነውን ይዞ ሄደ መልሶ አምጣ አለው እስኪ ከፍተህ እየው አለው ከፍቶ ቢያየው ጠጠር ገል አገኘ ንቀህ የተውኸውን ከፍተህ እየው አለው ከፍቶ ቢያየው ዝግግ ወርቅ አገኘ ያየኸው ምሳሌ ነው በአፍአ አጊጦ እንዳየኸው እኛም በሰው ዘንድ የከበርን ነን በውስጡ እንዲህ ያለ እንዳገኘህበት እኛም በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቅን የተዋረድን ነን ። ይህ የናቅኸው የባሕታዊ ምሳሌ ነው አንተ እንደ ናቅኸው እሱም በሰው ዘንድ የተናቀ ነው ። በውስጡ ዝግግ ወርቅ እንዳገኘህበት በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ የተወደደ ነው ። እንዲበልጠኝ አውቄ ነው እንጂ እንዲያው አድርጌዋለሁ መስሎሃል ብሎ ወርቁን አስይዞ ሰደደው ።

፲፮ ኦሪትኒ ወነቢያትኒ እስከ ዮሐንስ ሰበኩ እምትካት በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር ማቴ. ፲፩ ፡ ፲፪ ።

፲፮ ኦሪትም ነቢያትም ከጥንት ጀምረው የእግዚአብሔርን መንግሥት ነገር አስተማሩ ።
ወኵሉ ይትገፋዕ በእንቲአሃ ።
ሰው ሁሉ ስለርሷ ይገፋል ።

፲፯ ወባሕቱ ይቀልል ሰማይ ወምድር ይኅልፍ እምትደቅ አሐቲ ቃል እምኦሪት ወእምነቢያት ። ማቴ . ፭ ፡ ፲፰ ።

፲፯ ነገር ግን ከኦሪት ከነቢያት አንዲት ቃል ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል ።

፲፰ ወኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ ወያወስብ ካልዕተ ዘመወ ። ማቴ. ፭ ፴፪ ። ማር ፲፡፲፩ ። ፩ ቆሮንቶስ ፯ ፡ ፲ ።

፲፰ ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ አመነዘረ ።
ወዘኒ ያወስብ ኅድግተ ዘማዊ ውእቱ ።
የተፈታችውንም ያገባ ሴሰኛ ነው ።
ወእንተኒ ደኃራ ምታ ለእመ ቀርበት ካልዓ ዘመወት ባሏ የሞተባትም ሌላ ወንድ ብታገባ አመነዘረች ።

በእንተ ባዕል ።

፲፱ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ባዕል ወይለብስ ሜላተ ወሰየ ወልብሰ ቢሶስ ።
ሐተታ ስለ ሦስት ነገር ያመጣዋል ። ጽድቅ ቢሠሩ ዋጋ ኃጢአት ቢሠሩ ፍዳ እንዳይቀር ። ጻድቃን በፈቃዳቸው ኃጥአን ወዳሉበት ኃጥአንም በፈቃዳቸው ጻድቃን ወዳሉበት መሄድ መምጣት እንዳይቻላቸው ።

፲፱ ለመንገር ። ቀይ ሐር ነጭ ሐር ቀጭን ልብስ የሚለብስ ማለት ልልበስ ያለውን የማያጣ ።
ወይትፌሣሕ ወይትፈጋዕ ኵሎ አሚረ ።
ዕለት ዕለት ተድላ የሚያደርግ ነዌ የሚባል አንድ ባለጠጋ ነበር ። ሐተታ ስሙን የሚጽፍም የማይጽፍም ይገኛል ። ያልጻፈም እንደሆነ የተመቸ ከታወቀ ብሎ የጻፈ እንደሆነ አገረረበት ፍጡር ከሆነ ምንም ኃጥእ ቢሆን ከዲያብሎስ በቀር ፈጽሞ ጸናና የለምና ጥቂት ቅንነት ነበረችውና የዚህን ዋጋ በዚህ ዓለም ብዕለ ሥጋን ተቀብሏል ከጥቁር ላም አንድ ነጭ ጠጕር እንዳይጠፋ ።

፳ ወሀሎ ፩ ነዳይ ዘስሙ አልዓዛር ግዱፍ ውስተ ዴዴሁ ለባዕል ።

፳ ከነዌ ደጅ ወድቆ የሚኖር ። እንዘ ይደዊ በሕማመ ቊስል ቊስለ ሥጋ የታመመ አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው ነበር ።

፳፩ ወይፈቱ ይጽገብ እምፍርፋራት ዘይወድቅ እማዕዱ ለባዕል ።

፳፩ ከነዌ ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይመገብ ዘንድ የሚወድ ፍጡር ከሆነ ከመቤታችን በቀር ፈጽሞ ደግ የለምና ጥቂት ጽንነት ነበረችውና የዚያን ፍዳ በዚህ ዓለም ንዴተ ሥጋውን ተቀብሏል ።

ወከለባትኒ ይመጽኡ ወይልህሱ ቊሰሊሁ ።
ውሾቹም እየመጡ ቊስሉን ይልሱ ነበር ። ሐተታ የውሻው መላስ ልዝብ ነውና ደስ እያለው አይከለክላቸውም ነበር ።

፳፪ ወእምዝ ሞተ ዝኩ ነዳይ ።

፳፪ ከዚህ በኋላ አልዓዛር ሞተ ።
ወወሰድዎ መላእክት ውስተ ሕፅነ አብርሃም ።
መላእክት ወደ አብርሃም ጭን በአብርሃም ኪዳን ወደምትወረስ ወደገነት ወሰዱት ።
ወሞተ ባዕልኒ ። ነዌም ሞተ ።
ወተቀብረ ።
ተቀበረ ። ሐተታ አልዓዛርን ሞተ ብሎ ተቀበረ አላለውም በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም እንደሌለበት ለማጠየቅ ። ነዌን ግን ሞተ ብሎ ተቀበረ አለው በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም እንዳለበት ለማጠየቅ ።

፳፫ ወበሲኦልኒ አንሥአ አዕይንቲሁ እንዘ ሀሎ ውስተ ኵነኔ ወደያን ወርእዮ ለአብርሃም ርኁቀ ።

፳፫ በፍዳ ተይዞ በሲኦል ዓይኑን አራምዶ አብርሃምን በሩቅ አየው ።
ወአልዓዛርሃ ይረፍቅ ውስተ ሕፅኑ ።
አልዓዛርም ባጠገቡ ተቀምጦ ነበር ።

፳፬ ወጸውዖ ወይቤሎ ኦ አባ አብርሃም ተሣሃለኒ ።

፳፬ አብርሃም አባቴ ሆይ እዘንልኝ ።
ወፈንዎ ለአልዓዛር ከመ ይጥማዕ ጽንፈ አፅባዕቱ ማየ ወያቍርረኒ ልሳንየ ።
ጣቱን ከውኃ ነክሮ አንደበቴን ያቀዘቅዝልኝ ዘንድ አልዓዛርን ወደኔ ላክልኝ ።
እስመ ሐመምኩ ፈድፋደ በዛቲ እሳት ።
በዚህች እሳት ፈጽሜ ተቃጥያለሁና አለው ።

፳፭ ወይቤሎ አብርሃም ተዘከር ኦ ወልድየ ዘከመ ተፈጋዕከ ወተፈሣሕከ በሕይወትከ ።

፳፭ አብርሃምም ልጄ ሆይ በሕይወተ ሥጋ ሳለህ ተድላ ታደርግ እንደነበር ፤
ወአልዓዛርስ ከማሁ ከመ በተጽናስ ።

አልዓዛርም በችጋር እንደ ነበረ ዕወቅ አስብ አለው።
ወይእዜሰ ከማሁ ከመ ውእቱ ይትፌሣሕ በዝየ ።
ዛሬ ግን አንተ ተድላ ሥጋ ታደርግ እንደነበረ እርሱም ተድላ ነፍስ ያደርጋል ።
ወአንተሰ ተሐምም ።
እርሱም በንዴተ ሥጋ ይኖር እንደነበር አንተ በንዴተ ነፍስ ትኖራለህ ።

፳፮ ወምስለ ዝንቱ ኵሉ ጸድፍ ዓቢይ ይክልዓነ ማዕከሌነ ወማዕከሌክሙ ።

፳፮ ከዚህም ሁሉ ጋራ ታላቅ ገደል በእኛና በአንተ መካከል ይበለበለናል ማለት ጽኑ ፍትሐ እግዚአብሔር አለ ። ከመ እለሂ ይፈቅዱ ይኅልፉ እምለፌ ኢይክሀሉ መጺአ ኀቤክሙ ።
ከኛ ወደናንተ ማለፍ የሚወዱ መምጣት እንዳይቻላቸው ።
ወእለሂ መንገሌክሙ ኢይዕድው ኀቤነ ።
ከናንተም ያሉ ወደኛ እንዳያልፉ ። ኢንሬዕዮሙ ንሕነ ወእሙንቱ ኢይሬዕዩነ እስመ ጽልመት ሀሎ ማዕከሌነ ወኢየኃድገነ ንትርአይ በበይናቲነ ወይመስለኒ ከመ ሀሎነ ባሕቲትነ እንዘ ብዙኃ ጉባኤ ምስሌነ እንዲል ።

፳፯ ወይቤሎ እስእለከ አአባ አብርሃም ትፈንዎ ለአልዓዛር ቤተ አቡየ ።

፳፯ አብርሃም አባቴ ሆይ አልዓዛርን ወደ አባቴ ቤት ትልከው ዘንድ እለምንሃለሁ አለው።

፳፰ እስመ ሀለዉ ኃምስቱ አኃውየ ።
፳፰ አምስት ወንድሞች አሉኝና ።
ይንግሮሙ ወይሰምዑ ከመ ኢይምጽኡ እሙንቱሂ ውስተ ዛቲ ብሔረ ሕማም ፤
ነገራቸው ሰምተው ደግሞ ወደዚህች ስቃይ ሥፍራ እንዳይመጡ ፤

፳፱ ወይቤሎ አብርሃም ቦሙ ሙሴ ወነቢያት ኪያሆሙ ለይሰምዑ ።

፳፱ ሙሴ ነቢያትም አሏቸው እርሳቸውን ይስሙ ማለት ኦሪት ነቢያት አሉላቸው በርሳቸው ጸንተው ይኑሩ ። ወሙሴሰ ሕግ ውእቱ እንዲል ፤

፴ ወይቤሎ አልቦ አባ አብርሃም ፤
፴ እርሱም አባቴ አብርሃም ሆይ አይደለም።
አሐዱ እምነ ምውታን ለእመ ኢሖረ ኀቤሆሙ ወለእመ ኢነገሮሙ ኢየአምኑ ወኢይኔስሑ ።
ከሙታን አንዱ ወደርሳቸው ካልሄደ ካልነገራቸው አያምኑም አይመለሱም አለው ።

፴፩ ወይቤሎ አብርሃም ለእመሰኬ ሙሴሃ ወነቢያተ ኪያሆሙ ኢይሰምዑ ።

፴፩ አብርሃምም ሙሴን ነቢያትን ካልተቀበሉ፤ እመሂ ቦ ዘተንሥአ እምውታን ኢይሰምዕዎ ወኢየአምንዎ ።
ከሙታን ተለይቶ የተነሣም ቢኖር አያምኑም ሕገጋትን ካልተቀበሉ ከደጃቸው ወድቆ ይኖርየነበረ አልዓዛርንም አይቀበሉትም አለው ። ሐተታ ፡ ነዌ በብሉይ ነው ቢሉ የቀመቹ ምንም ጻድቃንን እደ እግዚአብሔር ቢጠብቃቸው ቦታ ያገናኛቸዋልና በሐዲስ ነው ቢሉ ነገሩ የሚያስኝ ስለ ሆነ አልዓዛር የእስራኤል ነዌ የፈርያን አምስቱ አኃው የኃምስ አብዳት ምሳሌ ።

ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ ላዕለ ዕቅፍት ።

ምዕራፍ ፲፯ ።

፩ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ግብር ይመጽእ መንሱት ። ማቴ፡፲፰፡፯ ማር፡፱፡፵፪።

፩ ለደቀ መዛሙርቱ አላቸው መከራ ግድ ይመጣል ።
ወባሕቱ አሌ ሎቱ ለዘያመጽአ ለመንሱት እምኀቤሁ ።
ነገር ግን መከራን ከራሱ ለሚያመጣት ሰው ወዮለት ።

፪ እምኃየሶ ይእስሩ ዐከሣዱ ማኅረፀ እድግ ወያስጥምዎ ውስተ ቀላየ ባሕር እምየስሕቶ ለአሐዱ እምእሉ ንኡሳን ።

፪ ከነሀ ከታናሾቹ አንዱን ከሚያስት የወፍጮ ደንጊያ ባንገቱ አስረው ከጥልቅ ባሕር ቢያሠጥሙት ይሻለው ነበር አላቸው ።

፫ ዑቁ ርእሰክሙ ። ሌዋ ፲፱፡፲፯ ሲራ ፲፱፡፲፫ ማቴ ፲፰፡፲፭ ።

፫ ለራሳችሁ ተጠበቁ ።
ለእመ አበሰ ለከ እኁከ ገሥጾ ለባሕቲቱ ።
ወንድምህ ቢበድልህ ለብቻው ተቆጣው ።
ወለእመኒ ነስሐ ኅድግ ሎቱ ።
ቢመለስም ይቅር በለው ።

፬ ወለእመኒ ስብአ ለለዕለቱ አበሰ ወስብዓ ለለዕለቱ ተጋነየ ኅድግ ሎቱ ።

፬ በቀንም ሰባት ጊዜ ቢበድል ሰባት ጊዜም ቢመለስ ይቅር በለው ። ሐተታ ማቴዎስ ሚመጠን እመ አበሰ ሊተ እኁየ እኅድግ ሎቱ አለው ይላል ። ሉቃስ እመኒ ስብዓ ለለዕለቱ አበሰ ወስብዓ ለለዕለቱ ተጋነየ ኅድግ ሎቱ አለው አለ እንደ ምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም እንደ ማቴዎስ ሚመጠን እመ አበሰ እትየ እኅድግ ሎቱ ቢለው

እመኒ ስብዓ ለለዕለቱ አበሰ ወስብዓ ለለዕለቱ ተጋንየ ኀድግ ሎቱ ብሎታል ከዚህ] በኋላ እስከ ስብእኑ ይላል አይብለከ እስከ ስብዕ አላ እስከ ፸ በበስብዕ ብሎታል አንድም ሚመጠነ እመ አበሰ እኁየ እኅድግ ሎቱ እስከ ስብዕኑ ቢለው አይብለከ እስከነ ስብዕ አላ እስከ ፸ በበስብዕ ብሎ ከዚህም ለእመ አበሰ ለከ እኁከ ስብዓ ጊዜያተ ወስብዓ ለለዕለቱ ትጋንየ ኀድግ ሎቱ ይላል ።

በእንተ ኀይል ዘሃይማኖት ወዘከመ ይደሉ ፈጽሞቱ ለግብር ።

፭ ወይቤልዎ ሐዋርያት ለእግዚእነ ወስከነ ሃይማኖተ ።

፭ ሐዋርያትም ጌታን ሃይማኖት ጨምርልን አሉት ሃይማኖት የሚጨምር መስሏቸው ። አንድም ይጨመራል የወጣነው ከማዕከላዊ ፡ የማዕከላዊ ከፍጹም ሲደርስ ይጨመራልና ። አንድም ተአምራት አድርግልን አሉት ሰው የሚያምንበት ስለሆነ ሃይማኖት አለው ።

፮ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እመ ብከሙ ሃይማኖት መጠነ ኅጠተ ሰናፔ ወትብልዋ ለዛቲ ሰግላ ተመልሒ እምሥርውኪ ወተተከሊ ውስተ ባሕርት ትኤዘዝ ለከሙ ።

፮ ጌታም አለ ሃይማኖትስ ቢኖራችሁ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል ይህችን ሾላ ተነቅለሽ ከባሕር ተተከይ ብትሏት ትታዘዝላችኋለች ።

፯ መኑ እምኔክሙ ዘቦ ገብር ሐረሳዊ ።
፯ ከናንተ ወገን ገበሬ ባርያ ያለው ።
ወእመኒ ኖላዊ ።
ጠባቂም ቢሆን ያለው ማነው
አቲዎ እምወፍሩ ።
ከተሰማራበት በተመለሰ ጊዜ ።
ይቤሎኑ እግዚኦ ዕርግ ነዓ ወርፍቅ ዝየ ።
ከኔ ጋር ተቀምጠህ ብላ ጠጣ ይለዋልን ።

፰ አኮኑ ይብሎ አስተዳሉ ሊተ ዘእዴሬር ።
፰ የምበላውን አዘጋጅልኝ ፡
ወቅንት ወመጥወኒ እስከ እበልዕ ወእሰቲ ።
ታጥቀህ የምበላውን የምጠጣውን አሳልፍልኝ ።
ወእምዝ ብላዕ ወስተይ አንተኒ ።
ከዚህ በኋላ አንተም ብላ ጠጣ ይለው የለምን ።

፱ ቦኑ እንጋ ምዝጋና ለውእቱ ገብር ለእመ ገብረ ዘአዘዞ እግዚኡ ።

፱ በውኑ ያባርያ ጌታው ያዘዘውን ቢያደርግ ይመሰግናልን ።

፲ ከማሁ አንትሙኒ ገቢረክሙ ኵሎ ዘአዘዝኩክሙ በሉ አግብርት ጽሩዓን ንሕነ ።

፲ እንደዚህም እናንተም ያዘዝኋችሁን ሥራ ሁሉ ሠርታችሁ ሥራ ፈት ባሮች ነን ።
ወዘይደልወነ ለገቢር ገበርነ ።
ልንሠራው የሚገባንን ሠራን በሉ ። አንድም የርትዑን ሠርተን የትሩፋቱ ቀርቶናል በሉ ።
በእንተ ፲ቱ እለ ለምጽ ።

፲፩ ወእምዝ እንዘ የሐውር ኢየሩሳሌም ኃለፈ ማዕከለ ሰማርያ ወገሊላ ።

፲፩ ከዚህ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በሰማርያና በገሊላ መካከል ሄደ ።

፲፪ ወእንዘ ይበውእ አሐተ ሀገረ ተቀበልዎ ዓሠርቱ ዕደው እለ ለምጽ ።

፲፪ ወደአንዲት አገር ሲገባ ለምጽ የያዛቸው ዐሥር ሰዎች ተገናኙት ።
ወቆሙ እምርኁቅ ።
ርቀው ቆሙ ።

፲፫ ወይቤሉ ወአውየው ኢየሱስ ሊቅ ተሣሃለነ ።

፲፫ ኢየሱስ መምህር ሆይ እዘንልን ብለው አሰምተው ተናገሩ ።

፲፬ ወርእዮሙ ወይቤሎሙ ሑሩ ኅበ ካህን ወአፍትኑ ርእሰክሙ

፲፬ አይቷቸው ከካህን ሄዳችሁ ራሳችሁን አስመርምሩ አላቸው ።
ወእንዘ የሐውሩ ነጽሑ ።
እርሳቸውም ሲሄዱ ዳኑ ነጹ ።

፲፭ ወርእዮ አሐዱ እምኔሆሙ ከመ ነጽሐ ተመይጠ እንዘ የአኵቶ ለእግዚአብሔር በዓቢይ ቃል ።

፲፭ ከርሳቸውም አንዱ እንደ ዳነ አይቶ እግዚአብሔርን በታላቅ ቃል እያመሰገነ ተመለሰ ። ሐተታ ያዳነኝን ትቼ ወዴት እሄዳለሁ ብሎ ።

፲፮ ወሰገደ ታሕተ እገሪሁ ለእግዚእ ኢየሱስ በገጹ ።

፲፮ ከጌታ እግር በታች በግንባሩ ሰገደ ።
ወአእኰቶ ። አመሰገነው ።
ወሳምራዊ ብእሲሁ ።
ትውልዱ ነገዱ ሳምራዊ ነው ።

፲፯ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ አኮኑ ዐሠርቱ እሙንቱ እንትሙ እለ ነጺሖሙ ።

፲፯ ጌታም አለ የዳናችሁት ዐሥር አልነበራችሁምን ።
አይቴኑ እንከ ተስዓቱ ።
ዘጠኙ ወዴት አሉ አለው ።

፲፰ ሎሙሰ ተስእናሙኑ ተመይጦ ወአዕኵቶ ለእግዚአብሔር ዘእንበለ ዝንቱ ዘካልዕ ሕዝቡ ።

፲፰ ወገኑ ልዩ ከሚሆን ከዚህ በቀር ተመልሶ እግዚአብሔርን ማመስገን ለርሳቸው ተሳናቸውን ።

፲፱ ወእምዝ ይቤሎ ተንሥእ ወሑር ሃይማኖትከ አሕየወተከ ።

፲፱ ተነሥተህ ሂድ ሃይማኖትህ አድኖሃልና። ሐተታ ዐሥሩ ለምጻሞች ያሥሩ ሕሊናት ምሳሌ የቀሩት ዘጠኙ የከፉ ሕሊናት ፤ የተመለሰው አንዱ የበጐ ሕሊና ምሳሌ ። ለአዳም ተውህብዎ ዐሠርቱ ሕሊናት ወለከሰ አሐዱ እንዲል ።

በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር ወበእንተ ተመይጦቱ ለወልደ ዕጓለ እምሕያው ።

፳ ወሶበ ተስእልዎ ፈሪሳውያን ወይቤልዎ ማዕዜ ትመጽእ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፳ ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች ማለት መቼ ትሰጣለች ብለው ጠየቁት።
ወአውሥአ ፤ መለሰ ።
ወይቤሎሙ ኢትመጽእ መንግሥተ እግዚአብሔር በተዓቅቦ ።
የእግዚአብሔር መንግሥት በጥንቃቄ አትሰጥም ።

፳፩ ወኢይብልዋ ነያ ዝየ ።
፳፩ ከወዲህ አለች ከወዲያ የለችም ።
ወነያ ከሀከ ።
ከወዲያ አለች ከወዲህ የለችም አትባልም ።
መንግሥተ እግዚአብሔር ነያ ማዕከሌክሙ ይእቲ።
የእግዚአብሔር መንግሥት እነሆ በመካከላችሁ ነች ማለት እኔን ማመን ነው ሲል ።

፳፪ ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ይመጽእ መዋዕል እመ ትፈትው ትርአዩ ፩ዐተ ዕለተ እምነ መዋዕሊሁ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

፳፪ ለደቀ መዛሙርቱ ከሰው ልጅ ቀኖች አንዲቱን ቀን ታዩ ዘንድ የምትመኙበት ቀን ይመጣል
ወኢትሬእዩ ።
ነገር ግን አታዩትም አላቸው ።

፳፫ ወለእመ ይብሉክሙ ነዋ ዝየ ወነዋ ከሀከ። ማቴ፡፳፫፡፳፬ ማር፡፲፫ ፤ ፳፩ ።

፳፫ እነሆ ከዚህ ነው ወይም ከዚያ ነው ይሏችኋል ።
ኢትሑሩ ። አትሂዱ።
ወኢትዴግኑ ። አትከተሉ።

፳፬ እስመ ከመ መብረቅ ዘይበርቅ ወያበርህ እምአጽናፈ ሰማይ እስከ አጽናፈ ሰማይ ከማሁ ውእቱ ይከውን ምጽአቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

፳፬ ከሰማይ ዳር እስከ ሰማይ ዳር እንደሚበርቅና እንደሚያበራ መብረቅ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና ።

፳፭ ወባሕቱ እምቅድመ ዝንቱ ኵሉ ብዙኀ የሐምም ወትሜንኖ ።

፳፭ አስቀድሞ ግን ብዙ መከራ ይቀበላል ወታሜክሮ ዛቲ ትውልድ ።
ይህችም ትውልድ ትፈታተነዋለች ።

፳፮ ወበከመ ኮነ በመዋዕሊሁ ለኖህ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ ለወልደ ዕጓለ እምሕያው ። ዘፍጥ፡፯፡፯ ማቴ ፳፬፡፴፯ ፤

፳፮ በኖኅ ዘመን እንደ ተደረገ የሰው ልጅ መምጣት እንዲህ ይደረጋል ።

፳፯ ወበከመ ኮነ እንዘ ይበልዑ ወይሰትዩ ያወስቡ ወይትዋሰቡ እስከ አመ ዕለት ቦአ ኖኅ ውስተ ኀፍቀ ታቦት ።

፳፯ ኖኅ ክፍል ወዳለው መርከብ እስከሚገባበት ቀን ድረስ ሲበሉ ሲጠጡ ሲያገቡ ሲጋቡ።
ወመጽአ ማየ አይኅ ወአጥፍአ ኵሎ ኀቡረ ።
የጥፋት ውኀ መጥቶ ሁሉንም እንዳጠፋ ።

፳፰ ወበከመ ኮነ በመዋዕሊሁ ለሎጥ ።
፳፰ በሎጥ ዘመን እንደ ተደረገ ።
እንዘ ይበልዑ ወይሰትዩ የሐንጹ ወይተክሉ
ዘፍ፡ ፲፱፡፳፭ ።
ሲበሉ ሲጠጡ ሲያንጹ ሲተክሉ ።
ይሠይጡ ወይሣየጡ ።
ሲገዙ ሲሸጡ እንደነበሩ ።

፳፱ እስከ አመ ዕለተ ወፅአ ሎጥ እምሰዶም።
፳፱ ሎጥ ከሰዶም እስከሚወጣበት ቀን ድረስ ወአዝነመ እግዚአብሔር እሳተ ወተየ እምሰማይ።
እግዚአብሔርም ከሰማይ እሳትና ዲን እስከሚያዘንምበት ቀን ድረስ ። ሐተታ እግዚአብሔር እሳት አዝንሚ ኣመላእክት ዲን ነስንሰዋል እንዲያጸናው።
ወአጥፍአ ኵሎ ።
ሁሉንም እስከሚያጠፋበት ቀን ድረስ ።

፴ ከማሁ ውእቱ ምጽአቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ኢይትዓወቅ ።

፴ የሰው ልጅ መምጣትም እንደዚሁ አይታወቅም ።

፴፩ ይእተ አሚረ ዘሀሎ ውስተ ናሕስ ።
፴፩ ያን ጊዜ በሰገነት ላይ ያለ ።
ወንዋዩ ውስተ ቤት ።
በቤት ያለ ገንዘቡንም ።
ኢይረድ ይንሣእ ።
ያንሣ ዘንድ አይውረድ ።
ወዘሂ ገዳመ ሀሎ ኢይግባእ ድኅሬሁ ።
በምድረ በዳም ያለ ወደኋላው አይመለስ ።

፴፪ ተዘከርዋ ለብእሲተ ሎጥ ።
፴፪ የሎጥን ሚስት አብነት አድርጓት ። ሐተታ መላእክት ይዘዋቸው ሲወጡ ዞረሽ አትዩ ብለዋታል ከወጣች በኋላ የእሳቱን ድምፅ ሰምታ ወይ አገሬ ሰዶም ብላ ዞራ ብታይ ሐውልተ ጼው ሆናለች ያጼው ክንቱ እንደሆነ እናንተም ከመነናችሁ በኋላ ወደ ዓለም ብትመለሱ ክንቱ ትሆናላችሁ ለማለት እንዲህ አለ ።

፴፫ ዘይፈቅድ ያድኅና ለነፍሱ ለይግድፋ ።
ማቴ፡፲፡፴፱ ማር፡፰፡፴፭ ሉቃስ ፱፡፳፬ ዮሐ፡፲፪፡፳፭።

፴፫ ሰውነቱን ሊያድናት የወደደ ሁሉ ይጣላት ።
ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ የሐይዋ ።
ሰውነቱንም ስለኔ የጣላት ያድናታል ።

፴፬ እብለከሙ በይእቲ ሌሊት ክልኤቱ ይሰክቡ ውስተ አሐዱ ዓራት ።

፴፬ በዚያች ሌሊት ሁለቱ በአንድ አልጋ ይተኛሉ ።
አሐዱ ይነሥኡ ።
አንዱን ይወስዳሉ ።
ወካልኦ የኀድጉ ።
ሁለተኛውንም ይተዋሉ ።

፴፭ ወክልኤቲ የኃርጻ በእሐቲ ማኅረጽ ።
፴፭ ሁለት ሴቶች ባንድ ወፍጮ ይፈጫሉ ።
እሐተ ይነሥኡ ።
አንዲቱን ይወስዳሉ ።
ወካልዕታ የኀድጉ ።
ሁለተኛይቱንም ይተዋሉ ።
ወክልኤቱ ይሄልዉ ውስተ አሐዱ ገራህት ።
ሁለቱ በአንድ እርሻ ይኖራሉ ።
አሐደ ይነሥኡ ።
አንዱን ይወስዳሉ ።
ወካልኦ የኀድጉ ።
ሁለተኛውን ይተዋሉ ።

፴፯ ወአውሥኡ ወይቤልዎ ኀበ አይቴኑ እግዚእ ።

፴፯ አቤቱ ወዴት ነው ብለው ጠየቁት ።
ወይቤሎሙ ኀበ ሀሎ ገደላ ህየ ይትጋብኡ አንስርት። ጥንብ ካለበት አሞሮች ይሰበሰባሉ አላቸው ።

በአንተ መኰንን አኩይ ።

ምዕራፍ ፲፰ ።

፩ ወመሰለ ሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ በምሳሌ ከመ ዘልፈ ይጼልዩ ወኢይትሀከዩ ሲራ ፲፰፡፳፪ ፩፡ ተሰ፡ ፭፡፲፯ ።

፩ ይጸልዩ ዘንድ ቸል እንዳይሉ ማለት ጸሎት መላልሶ መጸለይ እንዲገባ ፈጥኖ መተው እንዳይገባ ለጊዜው ሊያደርገው ያልወደደውን ተላጽቆተ ስኢል እንዲያደርግለት ምሳሌ መስሎ ይነግራቸዋል ።

፪ ወይቤሎሙ ሀሎአ አሐዱ መኰንን በአሐቲ ሀገር ዘኢይፈርሆ ለእግዚአብሔር ወኢያኃፍር ሰብአ ።

፪ ሰውን የማያፍር እግዚአብሔርን የማይፈራ አንድ ሹም በአንዲት አገር ነበር አላቸው

፫ ወሀለወት አሐቲ ዕቤርት በይእቲ ሀገር።
፫ አንዲት ደኃም እርሱ በተሾመበት አገር ነበረች ።
ወቦነት ትመጽእ ኀቤሁ ወትቤሎ ኰንነኒ እምዕድውየ ።
ወደሱ እየመጣች ከባለጋራዬ ፈርደህ አድነኝ ትለዋለች ።

፬ ወእበያ ወአጕንደያ ።
፬ ቸል አላት ።
፭ ወእምዝ ሀለየ በልቡ ወይቤ እመ ኢይፈርሆ ለእግዚአብሔር ወኢየኃፍር ሰብእ ።

፭ እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር ።
፮ ከመ ኢታንጥየኒ ዛቲ እቤር እትቤቀል ላቲ።
፮ ይህች ደሀ እንዳትዘበዝበኝ እፈርድላታለሁ አለ ።
ከመ ኢትምጽአ ወኢታስርኃኒ ዘልፈ ።
ዘውትር እየመጣች እንዳትዘበዝበኝ ።

፮ ወይበሎሙ እግዚእነ ስምዑ ዘይቤ መኰንነ ዓመፃ ።

፮ ጌታም አለ ግፈኛ መኰንን ያሰውን ስሙ። እግዚአብሔርን እንከ ኢይፈትሕኑ ለኅሩያኒሁ እለ ይግዕሩ ኀቤሁ መዓልተ ወሌሊተ ያስንኢ ለዚያች ድኃ እፈርድላታለሁ ያለ እንኪያ እግዚአብሔር በመዓልትም በሌሊትም ወደሱ ለሚለምኑ አይፈ

ርድላቸውምን ።
ወይትዔገሦሙኑ ።
ችል ይላቸዋልን ።

፰ እወ እብለክሙ ከመ ይፈትሕ ሎሙ ፍጡነ።
፰ አዎን ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል ብዬ እነግራችኋለሁ ።

ወባሕቱ ሶበ መጽአ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ይረክብኑ እንጋ ሃይማኖተ በዲበ ምድር ።

ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ ማለት ሰው በሆነ ጊዜ ሌላን ሃይማኖት አስተማረን ቃል ሥጋ ኮነ በሉ ብሎ አይደለምን አንድም ይረክቡኑ። በኋላ በመጣ ጊዜ ሌላን ይጠይቃል ቃል ሥጋ መሆኑ አውቃችኋልን አላወቃችሁም ብሎ አይደለምን ።

በእንተ ፈሪሳዊ ወመጸብሐዊ ።

፱ ወይቤሎሙ ለእለ ያጸድቁ ርእሶሙ ወይሜንኑ ቢጾሙ ።

፱ ባልንጀራቸውን ለሚንቁ ራሳቸውንም ለሚያከብሩ ሰዎች ።

፲ ወመሰለ ሎሙ ከመዝ ፤
ምሳሌ መስሎ ነገራቸው ።
ወይቤሎሙ ክልኤቱ ሰብእ ዐርጉ ቤተ መቅደስ ይጸልዩ ።

፲ ሁለት ሰዎች ወደ ቤተመቅደስ ሊጸልዩ ገቡ ። ወዓርጉ ቤተ አዎን ። ወዓርጉ ጴጥሮስ ወዮሐንስ ጊዜ ተሱዓት ሰዓት ለጸሎት እንዲል ።
አሐዱ ፈሪሳዊ ።
አንዱ ፈሪሳዊ ነው ። ፈሪሳዊ ማለት እሉል ባሕታዊ ማለት ነው ።
ወካልዑ መጸብሐዊ ።
አንዱ ቀራጭ ነው ።

፲፩ ወቆመ ፈሪሳዊ ወጼለየ ።
፲፩ ፈሪሳዊ ቁሞ ጸለየ ።
ወይቤ እእኵተከ እግዚኦ ዘኢረሰይከኒ ከመ ባዕዳን ሰብእ ።
እንደ ሌሎች ሰዎች ያላደረግኸኝ አቤቱ አመሰግንሃለሁ ።
ሐያድያን ። እንደሚቀሙ ።
ወዐማፅያን ። እንደሚበድሉ
ወእለ የሐውሩ ብእሲተ ብእሲ ፤
እንደሚያመነዝሩ ።
ወኢከመ ዝንቱ መጸብሐዊ ።
እንደዚህም ቀራጭ ያላደረግኸኝ ።

፲፪ እንሰ እጼውም ክልኤተ ዕለተ በኵሉ ሰናብት ።

፲፪ በሳምንት ሁለት ቀን እጾማለሁ ። ሐተታ እሑድና ማክሰኞ ወይም ማክሰኞና ሐሙስ ይጾማሉ።
ወአበውእ ዐሥራተ እዴሁ እምኵሉ ዘአጥረይኩ ።
ከገንዘቤ ሁሉ ካሥር አንድ እሰጣለሁ

፲፫ ወመጸብሐዊሰ ቆመ እምርሑቅ ።
፲፫ ቀራጭ ግን ከሩቅ ቆመ ።
ወኢፈቀደ ያንሥእ አዕይንቲሁ ላዕለ ውስተ ሰማይ።
ዓይኑን አቅንቶ ወደሰማይ ሊያይ አልወደደም ።
ወጕድዓ እንግድዓሁ ።

ደረቱን ይ.ቃ እንጂ ። ሐተታ መካን እእምሮ ነውና።
ወይቤ ስረይ ሊተ እግዚኦ ፤
አቤቱ ይቅር በለኝ አለ ።

እስመ አነ ኃጥእ ዘኢይደልወኒ እቁም ውስተ መካነ መቅደስከ ።

በምትመሰገንበት በቤተ መቅደስ መቆም የማይቻለኝ ኃጥእ ነኝና ።

፲፬ እብለክሙ ዝንቱ አተወ ቤቶ እንዘ ይጸድቅ እምዝኩ ሉቃስ ። ፲፬፥፲፩ ማቴ ፳፫፥፲፪ ።

፲፬ ይህ መጸብሐዊ ከፈሪሳዊ ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብሮ ተመለሰ ብዬ እነግራችኋለሁ ። አንድም እንዘ ይጼደቅ ይህ ፈሪሳዊ ተመጻድቆበት ሄደ ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።
እስመ ኵሉ ዘአዕበየ ርእሶ የኃሥር ።
ራሱን ያከበረ ሁሉ ይዋረዳልና ወዘአትሐተ ርእሶ ይከብር ።
ራሱን ያዋረደ ሁሉ ይከብራልና ።

በእንተ ኢየሱስ ወሕፃናት ።

፲፭ ወእምዝ አምጽኡ ኀቤሁ ሕፃናተ ከመ ያንብር እዴሁ ላዕሌሆሙ ። ማቴ. ፲፱፥፲፫ ማር. ፲፥፲፫

፲፭ እጁን ይጭንባቸው ዘንድ ሕፃናትን ወደሱ አመጧቸው ።
ወርእዮሙ አርዳኢሁ ገሠጽዎሙ ።
ደቀ መዛሙርቱም አይተው ቈጧቸው ።

፲፮ ወጸውዖሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ኅድጉ ሕፃናተ ይምጽኡ ኀቤየ ።

፲፮ ጌታም ጠርቶ አላቸው ሕፃናትን ወደኔ ይመጡ ዘንድ ተዋቸው ።
ወኢትከልእዎሙ ።
አትከልክሏቸው አላቸው ።
እስመ ለዘከመ እሉ ይእቲ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ላሉ ናትና

፲፯ አማን እብለክሙ ዘኢተቀበላ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ከመ ሕፃናት ኢይበውእ ፡

፲፯ የእግዚአብሔርን መንግሥት የማይቀበላት ሁሉ እንደ ሕፃናት አይገባባትም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

በእንተ ወሬዛ ባዕል ።

፲፰ ወተስእሎ አሐዱ መልአክ ። ማቴ፲፱፡፲፮።

፲፰ ካለቆች አንዱ ጠየቀው ።
ወይቤሎ ሊቅ ኄር ምንተ ሠናየ ገቢርየ እረክብ ሕይወተ ዘለዓለም ።
ቸር መምህር ሆይ ምን በጎ ሥራ ሠርቼ የዘላለም ሕይወትን አገኛለሁ አለው ።

፲፱ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ምንተ ትብለኒ ኄር ።

፲፱ ጌታም ለምን ቸር ትለኛለህ ።
አልቦ ኄር ዘእንበለ አሐዱ እግዚአብሔር ።
ካንድ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ቸር የለም ።

፳ ለሊከ ታእምር ትእዛዛቲሁ ።

፳ ትእዛዙን ታውቅ ዘንድ ።
ኢትቅትል ነፍሰ ።
ነፍስ አትግደል ።
ኢትሑር ብእሲተ ብእሲ ።
ወደ ጎልማሳ ሚስት አትሂድ
ወኢትዘሙ ።   አትሴስን ።
ወኢትሰርቅ ።   አትስረቅ ።
ወኢትኩን ሰምዓ በሐሰት ።
በሐሰት አትመስክር ።
ወአክብር አባከ ወእመከ ፡
አባት እናትክን አክብር ፡

፳፩ ወይቤሎ ዘንተሰ ኵሎ ዓቀብኩ እምን እስየ እስከ ይእዜ ።
ይህንስ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ እስከ ዛሬ ጠብቄ አለሁ ።

፳፪ ወሰሚዖ ዘንተ እግዚእ ኢየሱስ ይቤሎ አሐቲ ተርፈተከ ።

፳፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን ሰምቶ አንዲት ቀርታሃለች ።
ሑር ወሢጥ ኵሎ ዘብከ ንዋየ ወሀብ ለነዳያን ፡
ሂደህ ያለህን ገንዘብህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ ።
ወትረክብ መዝገበ ዘበሰማያት ።
በሰማይ መዝገብ ታገኛለህ ።
ወነዓ ትልወኒ ።
መጥተህ ተከተለኝ አለው ።

፳፫ ወሰሚዖ ዘንተ ተከዘ ፈድፋደ ።

፳፫ ይህን ሰምቶ ፈጽሞ አዘነ ።
እስመ ባዕል ውእቱ ጥቀ ወብዙኀ ጥሪቱ ።
እጅግ ባለጠጋ ነበር ገንዘቡም ብዙ ነበርና ።

፳፬ ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይቴክዝ ይቤ እፎ ዕፁብ ለእለ ቦሙ ንዋይ በዊአ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፳፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሲያዝን ባየው ጊዜ ገንዘብ ላላቸው ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት እንደምን ጭንቅ ነው አለ ።

፳፭ ይቀልል ገመል ይኅልፍ እንተ ሰቅረተ መርፍዕ እምባዕል ይባእ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፳፭ ባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማይ ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ሊያልፍ ይቀላል ፡

፳፮ ወይቤሉ እለ ሰምዑ መኑ ይክል ድኂነ

፳፮ ለሰሙትም መዳን ማን ይችላል አሉ ፡

፳፯ ወይቤሎሙ ዘበኀበ ሰብእ ይሰአን በኀበ እግዚአብሔር ይትከሃል ።

፳፯ በሰው ዘንድ የማይቻለው በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አላቸው ።

በእንተ ተላውያነ ኢየሱስ ።

፳፰ ወይቤሎ ጴጥሮስ ናሁ ንሕነ ኀደግነ ኵሎ ወተለውናከ ።

፳፰ ጴጥሮስም እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከትለንሃል ።
ምንተ እንጋ ንረክብ ።
ምን እናገኛለን አለው ።

፳፱ ወይቤሎሙ አማን እብለክሙ አልቦ መኑሂ ዘኃደገ ቤቶ ወአዝማዲሁ ወአኃዊሁ ወብእሲቶ ወውሉዶ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር።

፳፱ አባት እናቱን ወንድሞቹን ሚስቱን ልጆቹን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ብሎ የተወ ሁሉ በዚህ ዓለም ።

፴ ዘኢይነሥእ ዕሴቶ ብዙኃ ፤ተ ምክእቢተ በዝንቱ ዓለም ።

፴ ብዙ ዕጥፍ የማይወስድ የለም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።
ወበዓለምሰ ዘይመጽእ ሕይወተ ዘለዓለም ።
በሚመጣው ዓለም ግን የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛል ።

በእንተ ትንቢት ዘሕማማት ።

፴፩ ወእምዝ ነሥኦሙ እግዚእ ኢየሱስ ለዐሠርቱ ወክልኤቱ አርዳኢሁ ። ማቴ ፳፤፲፯ ማር ፲ ፤ ፴፪ ።

፴፩ ዐሥራ ሁለቱንም ደቀ መዛሙርቱን ወስዳቸው ።
ወይቤሎሙ ናሁ ነዓርግ ኢየሩሳሌም ።
እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን አላቸው ።
ወይትፌጸም ኵሉ ዘጽሑፍ ውስተ መጻሕፍተ ነቢያት ላዕለ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
በነቢያት መጽሐፍ የተጻፈው ሁሉ በሰው ልጅ ክርስቶስ ላይ ይፈጸማል ።

፴፪ ወይሜጥውዎ ለአሕዛብ ።
፴፪ ለአሕዛብም አሳልፈው ይሰጡታል ።
ወይሳለቁ ላዕሌሁ ።
ይዘባበቱበታል ።
ወይጼዕልዎ ፡ ይሰድቡታል
ወይዌርቁ ውስተ ገጹ ።
ይተፉበታልም ።

፴፫ ወይቀስፍዎ ፡ ይገርፉታል ።
ወይቀትልዎ ። ይገድሉታል ።

፴፫ ወይትነሣእ በሣልስት ዕለት ።
በሦስተኛው ቀን ይነሣል ።

፴፬ ወእሙንቱስ አልቦ ዘለበው እምዝ ይቤሎሙ ።

፴፬ እርሳቸው ግን የነገራቸውን አላወቁትም።
እስመ ስውር ውእቱ ዝንቱ ነገር እምኔሆሙ ወኢየአምሩ ዘይብል ።
ይህ ነገር ከርሳቸው ተሰውሮ ነበርና የሚናገረውን አያውቁም ነበር ።

በእንተ ዕውር ዘኢያሪኮ ።

፴፭ ወበጺሖሙ ኢያሪኮ ።
፴፭ ኢያሪኮ በደረሱ ጊዜ ።

ሀሎ አሐዱ ዕውር ይነብር ውስተ ፍኖት ወይስእል ማቴ፤፳፤፳፱-፴፭ ማር፤ ፲፤፴፮ ።
አንድ ዕውር ከመንገድ ተቀምጦ ይለምን ነበር።

፴፮ ወሰሚዖ ድምፀ ሰብእ ዘየኃልፍ ይቤ ምንትኑዝ ዘእሰምዕ ።

፴፮ የሚሄዱትን ሰዎች ድምፅ ሰምቶ ይህ የምሰማው ምድር ነው አለ ።
ወይቤልዎ ኢየሱስ ናዝራዊ የኃልፍ ።

፴፯ ወይቤልዎ ኢየሱስ ናዝራዊ የኃልፍ ።
፴፯ የናዝሬቱ እየሱስ እንዲያልፍ ነገሩት።

፴፰ ወአውየወ ወይቤ ኢየሱስ ወልደ ዳዊት ተሣሃለኒ ።

፴፰ የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ እዘንልኝ አለው
፴፱ ወገሠጽዎ እለ ይመርህዎ ከመ ያርምም።
፴፱ የሚመሩት ዝም እንዲል ተቆጡት ።
ወአውየወ ፈድፋደ ወይቤ ወልደ ዳዊት ተሣሃለኒ።
እሱ ግን የዳዊት ልጅ ሆይ እዘንልኝ ብሎ እጅግ ጮኸ ።

፵ ወቆመ እግዚእ ኢየሱስ ወአዘዘ ያምጽእዎ ኀቤሁ ።

፵ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቆሞ ወደርሱ ያመጡት ዘንድ አዘዘ ።
ወበጺሖ ኀቤሁ ይቤሎ ምንተ ትፈቅድ እግበር ለከ ።
ወደርሱም በደረሰ ጊዜ ምን ላድርግልህ ትወዳለህ አለው

፵፩ ወይቤሎ እግዚኦ ከመ ይርአያ አዕይንትየ።
፵፩ አቤቱ ላይ እወዳለሁ አለው ።
፵፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ርኢ ።
፵፪ ጌታም አለው እይ ።
ሃይማኖትከ አሕየወተከ ።
ሃይማኖትህ አዳነህ አለው ።

፵፫ ወርእየ ሶቤሃ ወተለዎ ።

፵፫ ያንጊዜም አይቶ ተከተለው ወአዕኰቶ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርንም አመሰገነው
ወርእዮሙ ኵሉ ሕዝብ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር።
ሕዝቡም ሁሉ አይተው አመሰገኑት ።

በእንተ ዘኬዎስ መጸብሐዊ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወበዊአ እግዚእ ኢየሱስ ኢያሪኮ አንሶሰወ።
፩ ኢያሪኮ ገብቶ መላልሶ አስተማረ ።

፪ ወናሁ ረከበ ብእሴ ዘስሙ ዘኬዎስ መልአኮሙ ለመጸብሓን ።

፪ እነሆ የቀራጮች አለቃ የሚሆን ዘኬዎስ የሚባል ሰው አገኘ ።
ወባዕል ውእቱ ።
ባለጸጋም ነበረ ።

፫ ወየኃሥሥ ይርአዮ ለእግዚእ ኢየሱስ ከመ ያእምሮ መኑ ውእቱ ።

፫ ማናቸው እንደሆነ ያውቅ ዘንድ ጌታን ሊያየው ይወድ ነበር ።
ወኢያበውሖ ሰብእ ።
ሰው ግን አያሳየውም ነበር ።
እስመ ሐጺር ውእቱ በቆሙ።
ቁመቱ አጭር ነበርና ።

፬ ወሮጸ ቅድሜሁ ወዓርገ ዲበ ሰግላ ።
፬ በፊቱ ሩጦ ከሾላ ላይ ወጣ ።
ከመ ይርአዮ ።
ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታን ያየው ዘንድ ።
እስመ እንተ ይእቲ ፍኖት ሀለዎ ይኅልፍ ።
በዚያች መንገድ ይሄድ ዘንድ አለውና ።

፭ ወበጺሖ ህየ ነጸሮ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ዘኬዎስ አፍጥን ወረድ ።

፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከዚያ በደረሰ ጊዜ አይቶ ዘኬዎስ ፈጥነህ ውረድ አለው ።
እስመ ዮም ሀለወኒ እዓል ቤተከ ።
ዛሬ ከቤትህ እውል ዘንድ አለኝና ፤

፮ ወአፍጠነ ወረደ ።
፮ ፈጥኖ ወረደ ።
ወአግኀዎ ኀበ ቤቱ እንዘ ይትፌሣሕ ።
ደስ ብሎት ከቤቱ አገባው ።
ሐተታ ይሄድብኛል ብሎ ።

፯ ወርእዮሙ ዘንተ አንጐርጐሩ ወይቤሉ ኀበ ብእሲ ኃጥእ ቦአ የዓል ።

፯ ሁሉም ባዩ ጊዜ ከኃጥእ ሰው ቤት ይውል ዘንድ ገባ ብለው ነቀፉት ።

፰ ወቆመ ዘኬዎስ ወይቤሎ ለእግዚእነ ናሁ እግዚእየ መንፈቀ ንዋይየ እሁብ ለነዳያን ።

፰ ዘኬዎስም ይህንን ሰምቶ ቁሞ ለጌታችን እነሆ ጌታዬ የገንዘቤን እኩሌታ ለድኃ እሰጣለሁ።
ወእመሂ ቦ ዘገፋእክዎ አፈድዮ ትርብዕተ ህየንተ አሐዱ ።
የበደልኩት ቢኖር በአንድ አራት እከፍለዋለሁ አለው ።

፱ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ዮምስ ሕይወት ኮነ ለሰብአ ዝንቱ ቤት ።

፱ ኢየሱስም አለው ዛሬስ ለዚህ ቤት ሰው ድኅነት ተደረገ ።
፲ እስመ አንተሂ ወልደ አብርሃም አንተ ።
፲ አንተም የአብርሃም ልጅ ነህና ።
እስመ መጽአ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ይኅሥሥ ወያድኅን ዘተኃጕለ ።
ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስም የጠፋውን ሊሻ የተጐዳውን ሊያድን መጥቷልና ።

በአንተ ምሳሌ ዘምናናት ።

፲፩ ወእንዘ ይሰምዑ ዘንተ መሰለ ሎሙ ወይቤሎሙ ።

፲፩ ይህን ሲሰሙ ምሳሌ መስሎ ነገራቸው
እስመ ቅሩብ ውእቱ ለኢየሩሳሌም ።
ለኢየሩሳሌም አቅራቢያ ነበርና ። ሐተታ ወሰብአ ሀገሩ ይጸልዕዎ ያለውን ይሻል ።
ወይመስሎሙ ከመ ሶቤሃ ታስተርኢ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
መንግሥተ ሰማያት ያን ጊዜ ፈጥና የምትሰጥ ይመስላቸው ነበርና ። ሐተታ አሐዱ ብእሲ ክቡር ሐረርትቀ ብሔረ ያለውን ይሻል ። አንድም ይህን ሲሰሙ ወእንዘ ይመስል ሎሙ ይላል እየመሰለ ሲነግራቸው መንግሥተ ሰማያት ትሰጥ ትገለጥ ባለ ጊዜ እንዳትውል እንዳታድር ፈጥና እንድትሰጥ ዕወቁ ። ይሰወጥ ያለውን ይሻል ።

፲፪ ወይቤ አሐዱአ እ ብእሲ ክቡር ሐረርትቀ ብሔረ ይንሣእ ሎቱ መንግሥተ ወይሰወጥ ።

፲፪ አንድ የከበረ ሰው መንግሥትን እጅ አድርጎ ይመለስ ዘንድ ወደሩቅ አገር ሄደ ።

፲፫ ወጸውዓ አግብርቲሁ ዐሡርተ ወወሀቦሙ ዓሠርተ ምናናተ ።

፲፫ ዐሥሩን ባሮቹን ጠርቶ ዐሥር ምናን ሰጣቸው ። ሐተታ ዐሥራ ሁለቱ ወቄት አንድ ነጥር ዐሥራ ሁለቱ ነጥር አንድ ምናን ዐሥራ ሁለቱ ምናን አንድ መክሊት ። መክሊቱ ሽ፻፸፪፳፰ ወቄት ይሆናል ።
ወይቤሎሙ ተገበሩ እንከ እስከ አዓቱ ።
እስክመለስ ድረስ ውጡበት ውረዱበት ብሎ ሰጣቸው ።

፲፬ ወሰብአ ሀገሩ ይጸልእዎ ፤
፲፬ ያገሩ ሰዎች ይጠሉት ነበር አይወዱትም ነበርና ።
ወፈነዉ ተናብልተ እምድኅሬሁ እንዘ ይብሉ ኢንፈቅዶ ለዝንቱ ይንግሥ ላዕሌነ ።
ይህ በኛ ላይ ሊነግሥብን አንወድም ብለው ከወደ ኋላው መልክተኞችን ላኩ ።

፲፭ ወእምዝ አተወ ነሢአ መንግሥተ ።
፲፭ ከዚህ በኋላ መንግሥትን እጅ አድርጎ ተመለስ ።
ወአዘዘ ያምጽእዎሙ ለአግብርቲሁ ዘወሀቦሙ ወርቀ ከመ ያእምር ዘከመ ተገበሩ ።
እንዴት እንዳተረፉ ያውቅ ዘንድ ወርቁን የሰጣቸውን ባሮቹን ያመጧቸው ዘንድ አዘዘ ።

፲፮ ወመጽአ ቀዳማዊ ወይቤሎ እግዚኦ ምናንከ ዐሠርቱ ።

፲፮ አንዱ መጥቶ አቤቱ ምናንህ ዐሥር ነበር ።
ወዐሠርተ ምናናተ ረባሕኩ ።
ዐሥር ምናን አተረፍኩ አለው ።

፲፯ ወይቤሎ እግዚኡ አኅብር ኄር ወምእመን ዘበውሑድ ምእመነ ኮንከ ላዕለ ብዙኅ እሰይመከ።

፲፯ አንተ የታመንክ በጐ ባሪያ በጥቂቱ ከታመንክ በብዙ ላይ እሾምሃለሁ ።
ተሠየም ላዕለ ዐሥሩ አህጉር ባሥሩ አገር ተሾም አለው በሥርቱን ቃላት ጠብቆ በሚገኝ ክብር መክበሩን መናገር ነው ።

፲፰ ወመጽአ ካልዑሂ ወይቤሎ እግዚእ ምናንከ ኃምስቱ ።

፲፰ ሁለተኛውም አቤቱ ገንዘብህ አምስት ምናን ነበር ።
ወኃምስተ ምናናተ ረባሕኩ ።
አምስት አተረፍኩ ።

፲፱ ወይቤሎ ሎቱኒ አንተኒ ተሠየም ላዕለ ኃምስቱ አህጉር ።

፲፱ እርሱን አንተም ባምስቱ አገር ተሾም አለው ። በአምስቱ አዕማደ ምሥጢር በሚገኝ ክብር መክበሩን መናገር ነው ።

፳ ወመጽአ ሣልሱኒ ወይቤሎ እግዚእ ነያ ምናንከ እንተ ኀቤየ እንበርክዋ ወጠብለልክዋ ፡ ውስተ ሰበንየ ።

፳ ሦስተኛም መጥቶ በመጠምጠሚያዬ የጠቀለልኳት ገንዘብህ እነሆ ይህች ናት ማለት ፡ ለራሴ ጠብቄ ለሌላው አላስተማርሁም ።

፳፩ እስመ ፈራህኩከ እስመ እእምረከ ከመ ዕፁብ ብእሲ አንተ ።

፳፩ የምታስጨንቅ ሰው እንደሆንህ ስላወቅሁ ፈርቻለሁና ።
ወትነሥእ ዘኢያንበርከ ።
ያላኖርከውን የምታነሣ ።
ወተአርር ዘኢዘራዕከ ።
ያልዘራኸውን የምትሰበስብ ጨካኝ እንደሆንክ ስላወቅሁ ።

፳፪ ወይቤሎ እግዚኡ በከመ ቃልከ እኴንነከ ኦ ገብር እኩይ ወወሐካይ ።

፳፪ አንተ ክፉ ሐኬተኛ ባሪያ እንደ ቃልህ እፈርድብሃለሁ ።

ተአምረኒኑ ከመ ዕፁብ ብእሲ አነ አነሥእ ዘኢያንበርኩ ወአአርር ዘኢዘራዕኩ ወአስተጋብእ ዘኢዘረውኩ ።
ያልበተንኩትን የምሰበስብ ያልዘራሁትን የማጭድ ያላኖርኩትን የማነሣ ጽኑ ጨካኝ መሆኔን ታውቃለህን ።

፳፫ ወለምንት ዘኢያግባእከ ወርቅየ ውስተ ማዕድየ ።

፳፫ ስለምን ገንዘቤን ወደለዋጮች ያላኖርህ ። ወለልየ አቲውየ እምአስተገበርክዎ ምስለ ረባሐ ። እኔ መጥቼ ለሚያስተርፍ እሰጠው ነበር ።

፳፬ ወይቤሎሙ ለእለ ይቀውሙ ህየ ንሥኡ እምላዕሌሁ ዘንተ ምናነ ወሀብዎ ለዘቦቱ ፲ቱ ምናናት ።

፳፬ ከዚያ ቆመው ያሉትን ይህን ገንዘብ ወስዳችሁ ዐሥር ላለው ስጡት አላቸው ።

፳፭ ወይቤልዎ እግዚእ እኮኑ ቦቱ ዐሠርቱ ምናናት ።

፳፭ አቤቱ ዐሥር ምናን ያለው አይደለምን አሉት ።

፳፮ ወይቤሎሙ እብለክሙ እስመ ለኵሉ ዘቦ ይሁብዎ ወይዌስክዎ ። ማቴ፡፲፫፡ ፲፪ ማር፡ ፬ ፡ ፳፭ ሉቃ፡ ፰ ፡ ፲፰ ።

፳፮ ላለው ሁሉ ይሰጡታል ይጨምሩለታልም። ወለዘሰ አልቦ አለኒ ቦ የሐይድዎ የሌለውን ግን ያለውንም ይወስዱበታል ።

፳፯ ወባሕቱ ለእልክቱስ ጸላዕትየ እለ ኢይፈቅዱ እንግሥ ላዕሌሆሙ አምጽእዎሙ ዝየ ወርግዝዎሙ በቅድሜየ ።

፳፯ ልነግሥባቸው የማይወዱ እኔህን ጠላቶቼን ግን አምጥታችሁ በፊቴ እየወጋችሁ ግሏቸው አለ ።

በእንተ በአተ ኢየሱስ ኀበ ኢየሩሳሌም ።

፳፰ ወዘንተ ብሂሎ እምልአ ቅድመ ወዓርገ ኢየሩሳሌም ።

፳፰ ይህንም ተናግሮ በፊታቸው ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ።

፳፱ ወሶበ በጽሐ ቤተ ፋጌ ። ማቴ፡፳፩ ፡ ፩ ማር፡፲፩ ፡ ፩

፳፱ ወደቤተ ፋጌም በቀረበ ጊዜ ፤
ወቢታንያ ኀበ ደብረ ዘይት ዘስሙ ኤሌዎን ።
ደብረ ዘይት ወደሚባል ቢታንያም በደረሰ ጊዜ ።
ፈነወ ፪ተ አምአርዳኢሁ ።
ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ ።

፴ ወይቤሎሙ ሑሩ ሀገረ ዘቅድሜክሙ ።
፴ ወደፊታችሁ ካለ አገር ሂዱ ።
ወበዊአክሙ ትረክቡ ዕዋለ ዕሱረ ዘኢተፅዕኖ ሰብእ ።

በገባችሁም ጊዜ ሰው ያልተቀመጠበት ያህያ ግልገል ታገኛላችሁ ።
ፍትሕዎ ወእምጽእዎ ሊተ ።
ፈትታችሁ አምጡልኝ ።

፴፩ ወእመቦ ዘይቤለክሙ ለምንት ትፈትሕዎ።
፴፩ ለምን ትፈቱታላችሁ የሚል ሰው ቢኖር ።
በሉ እግዚኡ ይፈቅዶ ።
ጌታው ይሻዋል በሉ ።

፴፪ ወሐዊሮሙ እለ ተፈነዉ ረከቡ በከመ ይቤሎሙ ።
፴፪ የተላኩትም እንደ ነገራቸው አገኙ ።
፴፫ ወፈትሑ ዕዋለ ።
፴፫ ያህያውን ግልገል ፈቱ ።
ወእንዘ ይፈትሑ ዕዋለ ይቤልዎሙ ኦጋእዝቲሁ ለምንት ትፈትሑ ዕዋለ ።
ያህያውን ግልገል ሲፈቱ ጌቶቹ ለምን ትፈቱታላችሁ አሏቸው ።

፴፬ ወይቤሉ እግዚኡ ይፈቅዶ ።
፴፬ ጌታው ይሻዋል አሉ ።
፴፭ ወነሥኡ ወወሰድዎ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ።
፴፭ ወደጌታችን ይዘውት ሄዱ ።
ወረነኑ አልባሲሆሙ ዲበ ዕዋል ።
ልብሳቸውን በአህያው ግልገል ላይ ጐዘጐዙ ።
ወአፅዓንዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ዲቤሁ ።
ጌታንም አስቀመጡት ።

፴፮ ወእንዘ የሐውሩ ነጸፉ አልባሲሆሙ ውስተ ፍኖት ።

፴፮ ሲሄዱም ልብሳቸውን ከመንገድ ይጐዘጕዙ ።

፴፯ ወበጺሖሙ ኀበ ሙራደ ዐቀብ ዘደብረ ዘይት ።

፴፯ ወደ ደብረ ዘይት በሚወርደውም መንገድ በደረሱ ጊዜ ሐተታ አፈ ቆላ ነው ከታች የመጣው አቀበቱን ወጥቶ የሚያርፍበት ከላይ የመጣ መጥቶ የሚያርፍበት ነው ከዚያ በደረሱ ጊዜ ።
አኀዙ ኵሎሙ አርዳኢሁ ይትፌሥሑ ወይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር በዓቢይ ቃል ።
ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ደስ ብሏቸው እግዚአብሔርን በታላቅ ቃል ያመሰግኑት ጀመር ።
በእንተ ኵሉ ኃይል ዘርእዩ ።
ስላዩት ኃይል ሁሉ ።

፴፰ እንዘ ይብሉ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ።

፴፰ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ እሱ የተባረከ ነው ።

ወቡሩክ ንጉሠ እስራኤል ።
የእስራኤልም ንጉሥ የተባረከ ነው ።
ሰላም በምድር ።
በምድር ሰላም ።
ወስብሐት በአርያም ።
በአርያምም ምስጋና እያሉ ።

፴፱ ወቦ እምፈሪሳውያን ወእምሕዝብ እለ ይቤልዎ ሊቅ ገሥጾሙ ለአርዳኢከ ።

፴፱ ከፈሪሳውያን ወገን ከሕዝቡ ወገን መምህር ሆይ ደቀመዛሙርትህን ተቆጣቸው ያሉትምአሉ።

፵ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ለእመ እርመሙ ።
እሉ እሎንቱ ኦእባን ይኬልሑ።
እኒህ ዝም ቢሉ እኒህ ድንጋዮች ይጮሀሉ ብሎ መለሰላቸው ።

፵፩ ወበጺሖ ርእያ ለሀገር በከየ ላዕሌሃ ።
፵፩ በደረስም ጊዜ አገሪቱን አይቶ ማለት የአይሁድን ስውነት አይቶ አለቀሰላት ።
፵፪ ወይቤላ ሶበሰ ተአምሪ ዮም ሰላምኪ ።
፵፪ አውቀሽስ ቢሆን የይቅርታሽ ቀን ዛሬ ነበር ።
ወባሕቱ እምይእዜሰ ተሰወረ እምአዕይንትኪ ።
ዛሬ ግን ከዕውቀት ተገተሻል ማለት አላወቅሽም እንጂ ።
፵፫ ወይበጽሕ መዋዕል አመ የዓግቱኪ ፀርኪ ።
፵፫ ጠላቶችሽ ከበውሽ የሚስፍሩብሽ ጊዜ ይደርሳል ።
ወይትአየኑኪ ላዕሌኪ ።
ይከትሙብሻል ።
ወየኃጽሩኪ ።
ይከቡሻል ።
ወያስተጋብኡኪ እምኵለሄ ።
ከራቱ ማዕዘን ይሰበስቡሻል ።

፵፬ ወይነጽሑኪ ለኪ ። ማቴ ፳፬ ፤ ፪ማር ፲፫፤፪ ሉቃ ፤ ፳፩ ፤ ፮ ።
፵፬ ይጥሉሻል ።
ወለውሉድኪኒ ምስሌኪ ።
ልጆችሽንም ካንች ጋራ እንዳንች ይጥሏቸዋል ።
ወኢየኃድጉ ዝየ እብነ ዲበ እብን በውስቴትኪ ።
ደንጊያንም በደንጊያ ላይ አይተውልሽም ።
እስመ ኢያእመርኪ መዋዕለ ሣህልኪ ።
የይቅርታሽን ወራት አላወቅሽምና ።

በእንተ ተሰዶቶሙ ለእለ ያረኵሱ ቤተ መቅደስ ።

፵፭ ወቦአ ምኵራበ ወሰደደ ኵሎ እለ ይሠይጡ ወይሣየጡ በቤተ መቅደስ ።
፵፭ ከምኵራብ ገብቶ በቤተ መቅደስ የሚሸጡትን የገዙትንም ሁሉ አስወጣ ።

ወገፍትዓ ማዕዳቲሆሙ ለመወልጣን ።
የለዋጮችንም ወንበር ገለበጠ ።
ወመናብርቲሆሙኒ ለእለ ይሠይጡ ርግበ ገንጸለ ።
ርግብ የማሸጡትንም ወንበር ገለበጠ ።

፵፮ ወይቤሎሙ ጽሑፍ ዘይብል ቤትየሰ ቤተ ጸሎት ይሰመይ ።

፵፮ ቤቴስ የጸሎት ቤት ይባላል የሚል ጽሑፍ አለ ።
ወአንትሙሰ ረሰይክምዎ በአተ ፈያት ወሠረቅት ።
እናንተ ግን የሌባ ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው ።

፵፯ ወኵሎ እሚረ ይሜህሮሙ በምኵራብ ።
፵፯ ዘወትር በምኵራብ ያስተምራቸው ነበር።
ወየኃሥሡ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ወሊቃናተ ሕዝብ በዘያቀትልዎ ።
የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎች የሕዝቡም አለቆች ይገሉት ዘንድ ይሹት ነበር ።

፵፰ ወኃጥኡ በዘይሬስይዎ ።
፵፰ የሚያደርጉትን አጡ ።
እስመ ኵሎሙ ሕዝብ ይሰቀሉ በአጽምዖቱ ።
ሕዝቡ ሁሉ ለትምህርቱ ይሳሱ ነበርና ።

ዘከመ ተሰእሎሙ ኢየሱስ በእንተ ጥምቀት ዘዮሐንስ ።

ምዕራፍ ፳ ።

፩ ወእምዝ አሐተ ዕለተ እንዘ ይሜህሮሙ ለሕዝብ በምኵራብ ወይነግሮሙ ቆሙ ላዕሌሁ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ወረበናት። ማቴ. ፳፩ ፡ ፳፫ ማር. ፲፩ ፡ ፳፯ ።

፩ ከዚህ በኋላ ባንድ ቀን በምኵራብ ለሕዝቡ ሲያስተምራቸው የምሥራችም ሲነግራቸው የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎች የሕዝቡም አለቆች ተነሡበት ።

፪ ወይቤልዎ ንግረነ በመባሕተ መኑ ትገብር ዘንተ ።

፪ በማን ሥልጣን ይኸን ትሠራለህ ።
ወመኑ አብሐከ ትግበር ከመዝ ።
እንዲህስ ታደርግ ዘንድ ማን አሠለጠነህ አሉት ።

፫ ወአውሥአ ወይቤሎሙ እሌአለክሙ እነሂ አሐተ ነገረ ።

፫ እኔም አንድ ነገር እጠይቃችኋለሁ ።
ወንግሩኒ ፤
እናንተም ንገሩኝ ።

፬ ጥምቀቱ ለዮሐንስ እምአይቴኑ ይእቲ ።
፬ የዮሐንስ ጥምቀቱ ከወዴት ናት ።
እምሰማይኑ ።
ከሰማይን ናት ።
ወሚመ እምሰብእኑ ።
ወይም ከሰው ናትን አላቸው ።

፭ ወተበሃሉ በበይናቲሆሙ ፤
፭ እርስ በራሳቸው እንዲህ አሉ ።
እመሂ ንብሎ እምሰማይ ይብለነ በእፎ ዘኢአመንክምዎ ።
ከሰማይ ነው ያልነው እንደሆነ ምነው ያላመናችሁበት ይለናል ።

፮ ወእመሂ ንብሎ እምሰብእ ይዌግሩነ ኵሉ ሕዝብ ።

፮ ከሰው ነው ያልነውም እንደሆነ ሕዝቡ ሁሉ ይጣሉናል ።
እስመ ኵሎሙ ተአመንዎ ለዮሐንስ ከመ ነቢይ ውእቱ ።
የሐንስ ነቢይ እንደሆነ ሕዝቡ ሁሉ አምነውታልና ።

፯ ወአውሥኡ ወይቤልዎ ኢነአምር እምኃበ ኮነት ።

፯ ከወዴት እንደሆነች አናውቅም ብለው መለሱ ።

፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እነሂ ኢይነግረክሙ በመባሕተ መኑ እገብር ከመዝ ።

፰ እኔም ይህን የምሠራ በማንም ሥልጣን እንደሆነ አልነግራችሁም አላቸው ።

በእንተ እኩያን ዐቀብተ ወይን ።

፱ ወአኃዘ ይመስል ሎሙ ለሕዝብ ዘንተ ምሳሌ ።

፱ ለሕዝቡም ይህን ምሳሌ ይመስልላቸው ጀመረ ።
ወይቤሎሙ ብእሲ ተከለ ወይነ ።
ሰው ወይን ተከለ ።
ወሤመ ሎቱ ዓቀብተ ለወይኑ ።
ለወይኑም ጠባቂ ሾመ ።
ወአከረየ ምክያደ ።
አውድማ አስቆፈረ ።
ወሐነጸ ማኅፈደ ።
ግንብም ሠራ ።
ወነገደ ርኁቀ ብሔረ ።
ወደሩቅ አገርም ሄደ ።
ወጕንደየ እቲወ ።
ብዙ ዘመንም ኖረ ።

፲ ወእመ ኮነ ጊዜ ፍሬሁ ፈነወ ገብሮ ኀበ ዓቀብተ ወይን ።

፲ በሚያፈራበት ጊዜ ባሪያውን ወደ ወይኑ ጠባቆች ላከ ።
ከመ ይፈንው ሎቱ እምፍሬ ወይኑ ።
ከወይኑ ይልኩለት ዘንድ ።
ወዘበጥዎ ዓቀብተ ወይን ለገብሩ ወፈነውዎ ዕራቆ ።
ወይን ጠባቆች ግን ባሪያውን ደብድበው ባዶውን ሰደዱት ።

፲፩ ወዳግመ ፈነወ ካልዓ ገብሮ ።
፲፩ ዳግመኛም ሌላውን ባሪያውን ላከ ።
ወኪያሁኒ ዘበጥዎ ወአሰርዎ ወፈነውዎ ዕራቆ ።
አርሱንም ኦስረው ደብድበው ባዶውን ሰደዱት ።
፲፪ ወካዕበ ፈነወ ሣልሳየ ገብሮ ።

፲፪ ዳግመኛም ሦስተኛውን ባሪያውን ላከ ።
ወኪያሁኒ ፈቀዕዎ ወወሰድዎ ።
እርሱንም እቁሰለው አባረሩት ።

፲፫ ወይቤ በዓለ ወይን ምንተ እንከ እሬሲ ።
፲፫ የወይኑም ባለቤት እንግዲህ ምን ላድርግ አለ ።
አፌኑ ወልድየ ዘአፈቅር ።
የምወደውን ልጄን እልካለሁ ።
ለእመ ኪያሁ የኃፍርዎ ርእዮሙ ።
እርሱን አይተው ያፍሩት እንደሆነ ብሎ ።
ወፈነዎ ፤ ላከው ።

፲፬ ወሶበ ርእይዎ ዓቀብተ ወይን ተማከሩ በበይናቲሆሙ ወይቤሉ ዝንቱ ውእቱ ወራሲሁ ።

፲፬ የወይኑ ጠባቂዎችም አይተው ወራሽ ልጁ ይህ ነው ።
ንዑ ንቅትሎ ወንርከብ ርስቶ ።
ኑ እርሱን ገድለነው ርስቱን እጅ እናድርግ ብለው መከሩ ።

፲፭ ወአውፅእዎ እፍአ እምዓጸደ ወይን ወቀተልዎ ።

፲፭ ከወይኑ ቦታ ውጭ አውጥተው ገደሉት ።
ወሶበ መጽአ በዓለ ዓጸደ ወይን ምንተ እንከ ይሬስዮሙ ።
የወይኑ ባለቤት በመጣ ጊዜ ምን ያደርጋቸዋል አላቸው ።

፲፮ ይመጽእ ወይቀትሎሙ ለእልከቱ ዓቀብተ ወይን ።

፲፮ መጥቶ የወይኑን ጠባቂዎች ይገድላቸዋል ።
ወይሁብ ወይናሂ ለካልዓን ዓቀብት ።
ወይኑንም ለሌሎች ጠባቆች ይሰጣል እንጂ አላቸው ።
ወሰሚዖሙ ቃሎ ይቤሉ ሐሰ ኢይከውን ከመዝ ።
ይኽነንም በሰሙ ጊዜ ይኽነንስ የሚያደርግ የለም አሉት ።

፲፯ ወነጸሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ምንትኑ ጽሑፍ ዘይብል እብን እንተ መነንዋ ነደቅት ይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማዕዘንት ። መዝ ፡ ፻፲፯ ፡ ፳፩ ኢሳ ፡ ፳፰ ፡ ፲፮ ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፵፪ ግብ ፡ ፬ ፡ ፳፩ ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፴፫ ፩. ጴጥ ፪ ፡ ፯ ።

፲፯ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወደርሳቸው አይቶ አናጾች የናቋት ድንጊያ የማዕዘን ራስ ሆነች የሚለው ጽሕፈት ምንድነው አላቸው ።

፲፰ ወኵሉ ዘወድቀ ዲበ ይእቲ እብን ይትቀጠቀጥ ።

፲፰ በዚያችም ደንጊያ ላይ የወደቀ ሁሉ ይሰበራል ።
ወለዘኒ ወድቀት ዲቤሁ ትቀጠቅጦ ወትደምቆ ።
የወደቀችበትንም ትሰብረዋለች ።

በእንተ ጸባሕት ዘቄሣር ።

፲፱ ወፈቀዱ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ከመ የአኃዝዎ ሶቤሃ ወፈርህዎሙ ለሕዝብ ።

፲፱ የካህናት አለቆችና ጸሐፎችም ያን ጊዜም ሊይዙት ወደው ሕዝቡን ፈሩዋቸው ።
እስመ አእመሩ ከመ በእንቲአሆሙ መሰለ ዘንተ ።
ይህንም ምሳሌ እንደ መሰለባቸው ዐውቀዋልና ።

፳ ወተግኅሥዎሙ እምኔሁ አጽንሑ ሎቱ እለ ይትዓቀብዎ ወፈነዉ ኀቤሁ ሰብአ ዓይን እለ ያጸድቁ ርእሶሙ ከመ ያስሕትዎ በቃሉ ። ማቴ. ፳፪ ፡ ፲፭ ማር ፡ ፲፪ ፡ ፲፫

፳ ጸድቃን መስለው በነገር ያጸምዱበት ዘንድ ተጠባባቂዎች አኖሩበት ።
ወከመ ያግብእዎ ለመኳንንት
ላለቆችም አሳልፈው ይሰጡት ዘንድ ፤
ወለመሳፍንት ፤
ለሹማምንቱም ፤

፳፩ ወተሰእልዎ ወይቤልዎ ሊቅ ነአምር ከመ ጽድቀ ትነግር ወትሜህር ።

፳፩ መምህር ሆይ እውነት እንድትናገር በውነትም እንድታስተምር ፤
ወኢታደሉ ለገጽ ወኢለመኑሂ ።
ፊት አይተህ ለማንም ለማን እንዳታደላ እናውቃለን አሉት ።

ወርትዓ ትሜህር ፍኖተ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርን መንግሥት በውነት ታስተምራለህ እንጂ ።

፳፪ ይከውነነሁ ነሀብ ጸባሕተ ለቄሣር ።
፳፪ ለቄሣር ግብር ልንሰጥ ይገባልን ፤
ወሚመ አልቦኑ ፤
ወይም አይገባምን ብለው ጠየቁት ፤

፳፫ ወአእመሮሙ ትምይንቶሙ ፤
፳፫ ተንኮላቸውን አውቆባቸው ፤
ይቤሎሙ ለምንት ታሜክሩኒ ።
ለምን ትፈትኑኛላችሁ ።

፳፬ አርእዩኒ አላደ ዲናሩ ።
፳፬ ወርቁን አሳዩኝ አላቸው ።
ወአምጽኡ ወአርአይዎ ፤
አምጥተው አሳዩት ።
ወይቤሎሙ ዘመኑ መልክዑ ወመጽሐፉ ።
ቅርጹ ጽሕፈቱ የማነው አላቸው ።
ወአውሥኡ ወይቤልዎ ዘቄሣር ።
የቄሣር ነው ብለው መለሱለት ።

፳፭ ወይቤሎሙ ዘቄሣር ሀቡ ለቄሣር ።
፳፭ የቄሣርን ለቄሣር ፤
ወዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ አላቸው ።

፳፮ ወስእንዎ አስሕቶቶ በቃሉ በቅድመ ኵሉ ሕዝብ ።

፳፮ በሕዝቡ ሁሉ ፊት በነገሩ ማሳት ተሳናቸው ወአንከሩ ማዕማአ አፉሁ ወአውሥኦቶ ወአርመሙ ። አከናውኖ መናገሩን ምላሹን ሰምተው አደነቁ ዝም አሉ ።

በእንተ ሰዱቃውያን ወበእንተ ትንሣኤ ሙታን ።

፳፯ ወመጽኡ ኀቤሁ ሰዱቃውያን እለ ይብሉ ኢየሐይዉ ምውታን ።

፳፯ ሙታን አይነሡም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደርሱ መጡ ።

፳፰ ወተስእልዎ ወይቤልዎ ሊቅ ሙሴ ጸሐፈ ለነ እንዘ ይብል ለአመቦ ብእሲ ዘሞተ እኁኁ ወኀደገ ብእሲቶ ።

፳፰ መምህር ሆይ ሰው ልጅ ሳይወልድ ቢሞት እንዘ አልቦ ውሉድ ።
ልጅ ሳይኖረው ።
ያውስባ እኁኁ ለብእሲቱ ወያቅም ዘርዓ ለእኁኁ ።
ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ ብሎ ሙሴ ጻፈልን ።

፳፱ ወሀለዉ እንከ ኀቤነ ሰብዓቱ አኃው ።
፳፱ ሰባት ወንድማማች ከኛ ዘንድ ነበሩ ።
ወአውሰበ ዘይልሕቅ ብእሲተ ወሞተ እንዘ አልቦ ውሉድ ።
ታላቁ ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ ።

፴ ወከማሁ አውሰባ ካልዑሂ ።
፴ ሁለተኛውም እንዲሁ አገባት ።
ወሣልሱሂ ነሥአ ከማሁ ።
ሦስተኛውም አገባት ።
ወኢኀደጉ ውሉደ ።
ልጅ ግን አልነበራቸውም ።

፴፩ ወእስከ ሰብዓቲሆሙ ከማሁ አውሰብዋ ወሞቱ እንዘ አልቦሙ ውሉድ ።

፴፩ ሰባቱም እንዲሁ አያገቧት ልጅ ሳይወልዱ ሞቱ ።

፴፪ ወድኅረ ኵሎሙ ሞተት ይእቲ ብእሲት ።
፴፪ ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ሞተች ።

፴፫ ወእመ የሐይ ው ሙታን ለመኑ እምኔሆሙ ትከውኖ ብእሲተ ።

፴፫ ሙታን በሚነሡበት ቀን ለማናቸው ሚስት ትሆናለች ።
እስመ ሰብዓቲሆሙ አውሰብዋ ።
ሰባቱም አግብተዋታልና ፤

፴፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፴፬ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ውሉደ ዝንቱዓለምያወስቡወይትዋሰቡ።
የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ ይጋባሉ ።
ይወልዱ ወይትዋለዱ ።
ይወልዳሉ ይዋለዳሉ ።

፴፭ ወእለሰ ይደልዎሙ ይረከብዎ ለዝክቱ ዓለም ።

፴፭ ያን ዓለም ይወርሱት ዘንድ የሚገባቸው ሰዎች ግን ።
እመ የሐይዉ ምውታን ኢያወስቡ ወኢይትዋሰቡ ።
ሙታን በሚነሡበት ጊዜ አያገቡም አይጋቡም ።

፴፮ ወኢይትከሃሎሙ እንከ መዊት ።
፴፮ ሁለተኛም ሞት የለባቸውም ።
አላ ከመ መላእክተ እግዚአብሔር በሰማያት እሙንቱ ።
እንደ መላእክት ይሆናሉ እንጂ ።
ወውሉደ እግዚአብሔር ይከውኑ ።
የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ ።
ወውሉደ ሕይወት እሙንቱ ።
የሕይወትም ልጆች ናቸው ።

፴፯ ወከመሰ የሐይዉ ምውታን ሙሴሂ ነገረ ዘከመ ይቤሎ እግዚአብሔር በኀበ ዕፀ ጳጦስ

አነ ውእቱ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ ። ዘፀ፥ ፫ ፡ ፮ ።

፴፯ ሙታን ግን እንዲነሡ በቍጥቋጦው ዘንድ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ እኔ ነኝ ብሎ እግዚአብሔር እንደ ነገረው ሙሴም ተናግሯል ።

፴፰ ኢኮነ አምላከ ምውታን ።
፴፰ እርሱም የሙታን አምላክ አይደለም ።
አላ አምላከ ሕያዋን ውእቱ ።
የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ ።
እስመ ኵሎሙ ሕያዋን እሙንቱ በኀቤሁ ።
በርሱ ዘንድ ሁሉም ሕያዋን ናቸውና ።

፴፱ ወአውሥኡ ሰብአ እምጸሐፍት ወይቤሉ ሊቅ ሠናየ ትቤ ።

፴፱ ከጸሐፊዎች ወገን የሚሆኑ ሰዎችም መምህር ሆይ መልካም ተናግረሃል ብለው መለሱ ።

፵ ወአልቦ እንከ መኑሂ ዘተሀበለ ይሰአሎ ።

፵ ማንም ማን ሊጠይቀው የወደደ የለም ።

ዘከመ ውእቱ መሲሕ ወልደ ዳዊት ።

፵፩ ወይቤሎሙ እፎኑ ይቤልዎ ለክርስቶስ ወልደ ዳዊት ።

፵፩ ክርስቶስን የዳዊት ልጅ እንደምን ይሉታል ።

፵፪ ወለሊሁ ይቤ በመጽሐፈ መዝሙር ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ እስከ አገብእሙ ለጸላእትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ ። መዝ ፡ ፻፱ ፡ ፩ ማቴ፡ ፳፪፡ ፵፬ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ።

፵፪ እርሱ ጌታዬ ጌታዬን ጸላቶችህን ከእግርህ በታች እስካደርግልህ በቀኜ ተቀመጥ አለው ።

፵፬ ዘለሊሁ እንከ ዳዊት እግዚእየ ይቤሎ እፎ እንከ ይከውኖ ወልዶ ።

፵፬ ዳዊት እርሱ ራሱ ጌታዬ ያለው እንደምን ልጁ ይሆናል ።

በእንተ ተመድልዎተ ዘጸሐፍት ።

፵፭ ወእንዘ ኵሎሙ ሕዝብ ይሰምዑ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ተዓቀብዎሙ ለጸሐፍት እለ ይፈቅዱ ያንሶስዉ ተላቢሶሙ ።

፵፭ ሕዝቡ ሁሉ ሲሰሙ ለደቀ መዛሙርቱ ረጅም ልብስ ለብሰው ከሚመላለሱ ተጠበቁ አላቸው ።
ወያፈቅሩ ተአምኆ በምሥያጥ ።
ባደባባይ እጅ ሊነሡዋቸው ከሚወዱ ።
ወነበረ ፍጽም በውስተ አዕዋዳት ።
ባደባባይ ፊት ለፊት መቀመጥ የሚወዱ ።
ወርእሰ ምርፋቃት በውስተ ምሳሐት ።
በምሳም ጊዜ በራስጌ መቀመጥን ከሚወዱ ።

፵፯ እለ ይውኅጥዎን ለአብያተ መበለታት ።
፵፯ የባልቴቶችን ገንዘብ ከሚበሉ ከጸሐፊዎች ተጠበቁ ።
ወይትሜየኑ በምክንያተ አንኅኆ ጸሎቶሙ ።
በምክንያት ጸሎታቸውን ያረዝማሉ ይተነኰላሉ ።
፵፯ እሙንቱ ይነሥኡ ዘየዓቢ ኵነኔ ።
፵፯ እኔህ ታላቅ ፍርድ ይቀበላሉ ።

በእንተ ጸሪቀ መበለት ነዳይት ።

ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወነጸረ አብዕልተ ዘያበውኡ መባዖሙ ውስተ ሙዳየ ምጽዋት ።

፩ መባቸውን ከምጽዋቱ ሣጥን የሚያገቡ ባለጸጎችን አየ ።

፪ ወርእየ ዕበረ መበለተ ዘአብአት ክልኤተ ጸራይቀ ።

፪ አንዲት ድኃ ባልቴትም ከዚያ ሁለት ነሐስ ስትጥል አየ ።

፫ ወይቤሎሙ አማን እብለክሙ ከመ ዛቲ ነዳይት ዕቤር አብዝኃት አብአ መባዐ ለእግዚአብሔር ።

፫ ይህች ድኃ ባልቴት ከሁሉ ይልቅ አብዝታ ለእግዚአብሔር መባዕ እንደሰጠች በውነት እነግራችኋለሁ ።

፬ እስመ እሉ ኵሎሙ እምተረፈሙ አብኡ መባዖ ለእግዚአብሔር ።

፬ እኒህ ሁሉ ከተረፋቸው ለእግዚአብሔር መባዕ ሰጥተዋልና ።
ወዛቲሰ ኵሎ ጥሪታ ዘባቲ አብአት ።
ይህች ግን ያላትን ገንዘብ ሁሉ ሰጥታለች ።

በእንተ ትንቢተ ጥፍአተ ቤተ መቅደስ ወሀገረ ኢየሩሳሌም ።

፭ ወቦ እለ ይቤልዎ በእንተ መቅደስ ሠናይ ዕበኒሁ ወሥርጋው ንድቁ ።

፭ ሕንጻው የተጌጠ ግንቡ ያማረ የቤተ መቅደስን ነገር የነገሩት አሉ ።

፮ ወይቤሎሙ ትሬእዩኑ ዘንተ ።
ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፪. ማር. ፲፫ ፡ ፪. ሉቃ ፲፱ ፡ ፵፬ ።

፮ ይሆን ታያላችሁ ።
ይመጽእ መዋዕል አመ ኢይትኃደግ ዝየ እብን ዲበ እብን ዘኢይትነሣእ ።
ደንጊያ በደንጊያ ላይ ሳይፈርስ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል ።

፯ ወተስእልዎ ወይቤልዎ ሊቅ ማእዜ ይከውን ዝንቱ ።

፯ መምህር ሆይ ይህ የሚደረገው ምን ጊዜ ነው
ወምንት ተአምሪሁ አመ ይከውን ዝንቱ ።
ይህ የሚደረግበትስ ምልክቱ ምንድነው ብለው ጠየቁት ።
ወይቤሎሙ ዑቁ ኢያስሕቱክሙ ።
እንዳያስቷችሁ አስተውሉ ።

፰ ወብዙኃን ይመጽኡ በስምየ እንዘ ይብሉ አነ ውእቱ ክርስቶስ ።

፰ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ ብዙ ሰዎች በስሜ ይመጣሉ ።
ወበጽሐ ዕድሜሁ ።
ዘመኑም ደርሷል እያሉ ይመጣሉ ።
ወኢትሑሩ ወኢትትልውዎሙ ። አትከተሏቸው ።

፱ ወአመ ሰማዕክሙ ቀትለ ።
፱ ሰልፍን ።
ወሐከከ ኢትደንግፁ ።
ጹብ ክርክር በሰማችሁ ጊዜም አትፍሩ ።
እስመ ይከውን ቅድመ ከመዝ ።
አስቀድሞ እንዲህ ይደረጋልና ።
ወባሕቱ አኮ ሶቤሃ ዘየኃልቅ ።
ነገር ግን ያን ጊዜ አይፈጸምም ።

፲ ወይቤሎሙ ይትነሥኡ ሕዝብ ዲበ ሕዝብ ።
፲ ሕዝብ በሕዝብ ላይ ።
ወነገሥት ዲበ ነገሥት ።
ነገሥታትም በነገሥታት ላይ ይነሣሉ ።

፲፩ ወይመጽእ ዓቢይ ረኃብ ወድልቅልቅ በበብሔሩ ።

፲፩ በየሀገሩም ታላቅ መናወጥ ረኃብ ይመጣል ።
ወፍርሃት ላዕለ ሰብእ ።
በሰውም ላይ ፍርሃት ።
ወተአምር ዓቢይ ይከውን ።
በሰማይም ታላቅ ምልክት ይሆናል ።

፲፪ ወእምቅድመ ዝንቱ ኵሉ ይእኅዙክሙ ወይወስዱክሙ አዕዋዳተ ።

፲፪ ከዚህ ሁሉ አስቀድሞ ይዘው ወደ ዐደባባይ ይወስዷችኋል ።
ወይሞቅሑክሙ ወይወስዱክሙ ኀበ ነገሥት በእንተ ስምየ ።
ስለ ስሜ እስረው ወደነገሥት ይወስዷችኋል ።

፲፫ ወዝንቱ ይረክበክሙ ከመ ይከውን ስምዐ ላዕሌሆሙ ።

፲፫ በርሳቸው ላይ ምስክር ሊሆናችሁ ይህ ይደርስባችኋል ።

፲፬ ዑቁ ኢተሀልዩ በልብክሙ ዘትብሉ ።
፲፬ የምትናገሩትን በልቡናችሁ እንዳታስቡ አስተውሉ ።

፲፭ እነ እሁበክሙ አፈ ወጥበበ በዘኢይክሉ ተዋሥአተክሙ ወተዋቅሥተክሙ እለ ይትነሥኡ ላዕሌክሙ ፤

፲፭ የሚነሡባችሁ እናንተን መከራከርና መቋቋም በማይቻላቸው ገንዘብ እኔ አፍና ጥበብ እሰጣችኋለሁና ፤

፲፮ ወያገብኡክሙ አዝማዲክሙ ወአኃዊክሙ
፲፮ ወንድሞቻችሁና አባቶቻችሁ ።
ወአዕርክቲክሙ ወቢጽክሙ ።
ወዳጆቻችሁና ባልንጀሮቻችሁም አሳልፈው ይሰጧችኋል ።

፲፯ ወኵሉ ይጸልኡክሙ በእንተ ስምየ ።
፲፯ በስሜ ስለ አመናችሁ ሁሉ ይጠሏችኋል ።
ወይቀትሉክሙ ።   ይገድሏችኋል ።

፲፰ ወኢትትኃጐል አሐቲ እምሥእርተ ርእስክሙ ፤

፲፰ ከራሳችሁ ጠጕር አንዲቱ አትጠፋም ፤
፲፱ ወበትዕግሥትክሙ ታጠርይዋ ለነፍስክሙ ።
፲፱ በትዕግሥታችሁ መከራውን ታግሣችሁ በመቀበላችሁ ነፍሳችሁን ታድንዋታላችሁ ጥሪት ታደርጓታላችሁ ።

ዘከመ በዓይ ጥፍአታ ለኢየሩሳሌም ወሕዝብ ።

፳ ወአመ የዐግትዋ ሠራዊት ለኢየሩሳሌም ።
ዳን ፱ ፣ ፳፯ ማቴ. ፳፬ ፤ ፲፭ ማር. ፲፫ ፤ ፲፬ ።

፳ ኢየሩሳሌምን ሊከቧት ባያችሁ ጊዜ የምትጠፋበት ጊዜ እንደ ደረሰ ዕወቁ ።

፳፩ ወይእተ አሚረ እለ ውስተ ይሁዳ ይጐዩ ውስተ አድባር ።

፳፩ ያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደተራራ ይሸሹ ።
ወእለሂ ማእከላ ይወፅኡ እምኔሃ ።
በመካከሏም ያሉ ከእሷ ይወጣሉ ።

፳፪ ወእለ ውስተ በሐውርቲሃ ኢይበውእዋ ።
፳፪ ባውራጃዋም ያሉ ወደርሷ አይገቡም ።

እስመ ዕድሜሃ ውእቱ በዘይትቤቀልዋ ።
በሚፈርዱባትገንዘብ ይፈርዱባት ዘንድ ጊዜዋ ነውና።
ከመ ይብጻሕ ኵሉ ዘጽሑፍ ላዕሌሃ ።
በርሷ የተጻፈው ሁሉ ይደርስባት ዘንድ ።

፳፫ ወባሕቱ አሌ ሎን ለፅኑሳት ወለለ የሐፅና በውእቱ መዋዕል ።

፳፫ ነገር ግን ለፀነሱ በዚያ ወራት ለሚያሳድጉም ወዮላቸው ።
እስመ ይከውን ዓቢይ ምንዳቤ በዲበ ምድር ።
በምድር ጽኑ መከራ ይሆናልና ።
ወመቅሠፍት ዲበ ዝንቱ ሕዝብ ።
በዚህም ሕዝብ ላይም መቅሠፍት ።

፳፬ ወይወድቁ በኲናት ።
፳፬ በጦርም ይወድቃሉ ።
ወይፄወው ውስተ ኵሉ አሕዛብ ።
ወደ አሕዛብ ይማረካሉ ።
ወይከይድዋ አሕዛብ ለኢየሩሳሌም ።
አሕዛብ በኢየሩሳሌም ይሰፍሩባታል ።
እስከ ይበጽሕ ዕድሜሆሙ ለአሕዛብ ።
የአሕዛብ ዘመናቸው እስኪፈጸም ድረስ አለ በሐሳዊ መሲሕ ጊዜ ቢሉ ፫ ዓመት ከ፫ ወር ነው ።

በእንተ እለ ይቀድሙ ትእምርታት ዘዕለተ ደይን ወደኀሪት ምጽአቱ ለኢየሱስ ።

፳፭ ወይከውን ተአምር ውስተ ፀሐይ ወወርኀ ኢሳ. ፲፫፥ ፲ ሕዝ. ፴፪፥፯ ኢዮ. ፪፥፲ ማቴ. ፳፬ ፡ ፳፱ ፡ ማር. ፲፫ ፳፬ ።

፳፭ በፀሐይና በጨረቃ ምልክት ይሆናል ።
ወከዋክብትኒ ይወድቁ እምሰማይ ዲበ ምድር ።
ከዋክብትም ከሰማይ ወደምድር ይወድቃሉ ።
ወይትመነደቡ አሕዛብ ወየኀሥሩ እምድምፀ ባሕር ።
አሕዛብም ከውቅያኖስ ድምፅ የተነሣ ይጨነቃሉ ይሸበራሉ ።

፳፮ ወትወፅእ ነፍስ ዕጓለ እመሕያው እምፍርሃት ወእምትሕዝብት ዘይመጽእ ለዓለም ።

፳፮ የሚመጣውን መከራ ከመመልከትና ከፍርሃት የተነሣ የሰው ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች ።
እስመ ይትከወስ ኃይለ ሰማያት ይእተ አሚረ ።
የዚያን ጊዜ የሰማዮች ኃይል ይናወጣልና ፤

፳፯ አሜሃ ይሬእይዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዘ ይመጽእ በደመና ሰማይ ምስለ ኃይል ብዙኅ ወስብሐት ።

፳፯ ያን ጊዜ የሰው ልጅ ከታላቅ ኃይልና ምስጋና ጋራ በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል ።

፳፰ ወአመ ኮነ ዝንቱ ኵሉ ስግዱ ወአንሥኡ ርእሰክሙ ። ሮሜ. ፰ ፡ ፳፫ ።

፳፰ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላም የመረታ ስግደት ስገዱ ራሳችሁን አንሡ አለ እንደ አባ በትረ ማርያም ። ቅዱሳን ከበቁ በኋላ የሚሠሩትን አያውቁትም እንደ እንዝርት ራስ ይዞራሉ ።
እስመ በጽሐ ዘያድኅነክሙ ።
የሚያድናችሁ ደርሷልና ።

ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ተደልዎት ለምጽአተ ክርስቶስ ኩናኒ ።

፳፱ ወመሰለ ሎሙ ወይቤሎሙ እምከመ ርኢክምዋ ለበለስ ወለኵሉ ዕፀው ከመ ሠረጹ ተአምሩ ከመ አልጸቀ ማዕረር ።

፳፱ በለስን ዛፍም ሁሉ እንደ ለመለመ ያያችሁ እንደሆነ መከር እንደ ደረሰ ዕወቁ ።

፴ ከማሁ አንትሙኒ እምከመ ርኢክሙ ከመ ኮነ ዝንቱ ለእምሩ ከመ በጽሐት መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፴ እናንተም ይህ ሁሉ እንደ ተደረገ ያያችሁ እንደሆነየእግዚአብሔርመንግሥት እንደቀረበች ዕወቁ

፴፩ አማን እብለክሙ ከመ ኢተኃልፍ ዛቲ ትውልድ እስከ አመ ይከውን ዝንቱ ኵሉ ።

፴፩ ይህ ሁሉ እስኪደረግ ይህች ትውልድ አታልፍም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፴፪ ሰማይ ወምድር የኃልፍ ።
፴፪ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ።
ወቃልየሰ ኢየኃልፍ ።
ቃሉ ግን አያልፍም ።

ዘከመ ይደልዎሙ ለክርስቲያን ተደልዎ ለሞት ።

፴፫ ዑቁ ርእሰክሙ ኢታክብዱ ልበክሙ በስታይ ወበፈጊዕ ወበህልዮ መንበርት ።

፴፫ በመብል በመጠጥ ይኽንንም ዓለም በማሰብ ልቡናችሁን እንዳታጠኑ ዕወቁ ።

፴፬ ወትበጽሐክሙ ይእቲ ዕለት ከመ መሥገርት እንተ ትወርድ ዲበ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ዲበ ምድር ።

፴፬ በምድር ባሉ በአዕዋፍ ወጥመድ ድንገት እንዲመጣባቸው ያች ቀን ድንገት ትደርስባችኋለች

፴፭ ትግሁ እንከ በኵሉ ጊዜ ።
፴፭ በጊዜው ሁሉ ተግታችሁ ጸልዩ ።

ከመ ትክሃሉ አምሥጦ በጸሎትክሙ እምነ ዝንቱ ኵሉ ዘይመጽእ ።
በምትጸልዩት ጸሎት ከዚህ ከሚመጣው መከራ ሁሉ መዳን ይቻላችሁ ዘንድ ።
ወትቁሙ ቅድሜሁ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
በወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ፊት መቆም ይቻላችሁ ዘንድ ።

፴፯ ወኮነ መዓልተ ይውዕል በምኵራብ ወሌሊተ ይወፅእ ወይበይት ውስተ ደብረ ዘይት ዘስሙ ኤሌዎን ።

፴፯ ቀን በምኵራብ ሲያስተምር ሌሊት ኤሌዎን በሚባል በደብረ ዘይት ሲጸልይ ያድር ነበር ።

፴፰ ወኵሉ ሕዝብ ይገይሡ ኀቤሁ ውስተ ምኵራብ ወያጽምዕዎ ቃሎ ።

፴፰ ሕዝቡ ሁሉ ትምህርቱን ይሰሙት ዘንድ እርሱ ወዳለበት ወደ ምኵራብ ማልደው ይሄዳሉ ።

በእንተ ምክር ዘ፸ ወ፪ቱ ፈታሕያን ላዕለ ኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፳፪ ።

፩ ወቀርበ በዓለ መጸለት ዘስሙ ፋሲካ ።
ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፪. ማር ፲፬ ፡ ፩ ።

፩ ፋሲካ የሚባለው በዓለ ናዕትም ቀረበ ።

፪ ወየኀሥሡ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት በዘይቀትልዎ ።

፪ የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎችም ይገድሉት ዘንድ ፈለጉ ።
ወኮኑ ይፈርህዎሙ ለሕዝብ ።
ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ ።

በእንተ ተሰናዕዎቱ ለይሁዳ ምስለ አይሁድ ።

፫ ወቦአ ሰይጣን ውስተ ልበ ይሁዳ አስቆሮታዊ ዘእምዓሠርቱ ወክልኤቱ ኍልቍ ። ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፲፬ ማር ፡ ፲፬ ፡ ፲ ።

፫ ቍጥሩ ካሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በሚሆን በይሁዳ ልብ ሰይጣን አደረበት ። ሐተታ ተለይቶን ያውቃል ሥራ አሠራው ሲል እንዲህ አለ ።

፬ ወሖረ ወተናገሮሙ ለሊቃነ ካህናት ወለጸሐፍት ከመ ያግብኦ ሎሙ ።

፬ ሄዶ ያሲዛቸው ዘንድ ከካህናት አለቆችና ከጸሐፊዎችም ጋራ ተነጋገረ ።

፭ ወተፈሥሑ ወተሰነዓው ምስሌሁ ወተናገርዎ የሀብዎ ፴ ብሩረ ።

፭ ደስ ብሏቸው ሠላሳ ብር እንሰጥሃለን ብለው ተነጋገሩት ።
ወአስተኃለቁ ነገረ ።
ነገር ቆረጡ ።

፮ ወተፈሥሐ ውእቱኒ ወየኀሥሥ ሳህተ ያግብኦ ሎሙ እንዘ አልቦ ሰብእ ።

፮ እሱም ደስ አለው ሰው ሳይኖር ያሲዛቸው ዘንድ ምቹ ቦታ ይሻ ነበረ ።

በእንተ ደኅሪት ድራር ወበእንተ አስተዳልዎት ።

፯ ወበጽሐት ዕለተ መጸለት ዘስሙ ፋሲካ አመ ይጠብሑ ፍሥሐ ።

፯ ፋሲካ ያርዱበት የነበረ በዓለ ናዕትም ደረሰ ።

፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ወለዮሐንስ ሑሩ ወአስተዳልው ለነ ፍሥሐ ዘንበልዕ ።

፰ ጌታም ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስና ዮሐንስን ሂዳችሁ የምንበላውን ፋሲካ አዘጋጁ አላቸው ።

፱ ወይቤልዎ በአይቴ ትፈቅድ ናስተዳሉ ለከ ፍሥሐ ።

፱ በግዐ ፋሲካውን ወዴት ልናዘጋጅልህ ትወዳለህ አሉት ።

፲ ወይቤሎሙ በዊአክሙ ሀገረ ትረክቡ ብእሴ ዘይጸውር ፃሕበ ማይ ።

፲ ወደ ሀገር በገባችሁ ጊዜም የውኃ ማድጋ የተሸከመ ታገኛላችሁ ።
ወትልውዎ ኪያሁ ኀበ ቦአ ቤተ ።
እርሱ ወደሚገባበት ቤት ተከተሉት ።

፲፩ ወበልዎ ለበዓለ ውእቱ ቤት ይቤለከ ሊቅ አይቴኑ ኀበ እበልዕ ፍሥሐ ምስለ አርዳእየ ።

፲፩ የዚያን ቤት ባለቤት ከደቀ መዛሙርቴ ጋራ ፋሲካውን የምንበላበት የት ነው አለህ መምህር በሉት ።

፲፪ ወውእቱ ያርእየክሙ ጽርሐ ዓቢየ ወንጹፈ ወስርግወ ።

፲፪ እርሱ የተነጠፈ ያጌጠ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል ።
ወበህየ አስተዳልው ለነ ፤
በዚያ አዘጋጁልን ።

፲፫ ወሖሩ ረከቡ በከመ ይቤሎሙ ።
፲፫ በሄዱም ጊዜ እንደ ነገራቸው አገኙት ።
፲፬ ወአስተዳለው ፍሥሐ ።
ፋሲካውን አዘጋጁ ።

በእንተ ሠሪዓ ቅዱስ ቍርባን ።

፲፬ ወሶበ ኮነ ጊዜሁ ለድራር ረፈቀ እግዚእ ኢየሱስ ወዐሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያቲሁ ምስሌሁ። ማቴ፡ ፳፮፥፳ ማር ፥ ፲፬፥፲፯ ።
ጊዜውም በደረሰ ጊዜ ጌታ ከርሳቸው ጋራ ለመብላት ተቀመጠ ።

፲፭ ወይቤሎሙ ፈቲወ ፈተውክዎ ለዝንቱ ፋሲካ እብላዕ ምስሌክሙ ።

፲፭ ይህን ፋሲካ ከናንተ ጋራ እበላ ዘንድ መውደድን ወደድኩ አላቸው ።
ዘእንበለ ይብጽሐኒ ሕማምየ ።
ከመከራዬ አስቀድሞ ።
ወነሥአ ኅብስተ እዕኵተ ወፈተተ ወወሀቦሙ ወይቤሎሙ ።
ዳቦውን አንሥቶ አመስግኖ ቆርሶ ሰጣቸው ።

፲፮ እብለክሙ ባሕቱ ከመ ኢይበልዕ እንከ እምኔሁ እስከ ይትፈጸም በመንግሥተ እግዚአብሔር ።

፲፮ በእግዚአብሔር መንግሥት እስኪፈጸም ድረስ ከርሱ እንግዲህ አልበላም ብዬ እነግራችኋለሁ አላቸው ።

፲፯ ወተመጦ ጽዋዐ ወእዕኵተ ።
፲፯ ጽዋውንም ተቀብሎ አመስግኖ
ወይቤሎሙ ንሥኡ ዘንተ ወተካፈልዎ ዠልክሙ ።
ይህን ተቀበላችሁ ሁላችሁ ተካፈሉት ።

፲፰ እብለክሙ እንሰ ኢይሰቲ እንከ እምዝንቱ እጺረ ፍሬ ወይን እስከ እመ እሰትዮ በመንግሥተ እግዚአብሔር ።

፲፰ በእግዚአብሔር መንግሥት እስክጠጣው ድረስ ከዚህ ወይን ጭማቂ አልጠጣም ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፲፱ ወእምዝ ነሥአ ኅብስተ ወእዕኵተ ፩፥ ቆሮ ፲፩፥፳፬ ።

፲፱ ኅብስቱን ይዞ አመስግኖ ።
ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ።
ቆርሶ ሰጣቸው ።
ወይቤሎሙ ዝንቱ ውእቱ ሥጋየ ዘይትወሀብ በእንቲአክሙ ለቤዛ ብዙኃን ።
ለብዙ ሰዎች ቤዛ ስለናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ይህ ነው ።
ወከመዝ ግበሩ ተዝካርየ በእንቲአየ ።
መታሰቢያዬን እንዲህ አድርጉ

፳ ወከማሁ ጽዋዓኒ እምድኅረ ተደሩ
፳ ጽዋውንም እንዲሁ ከበሉ በኋላ ሰጣቸው ።
ወይቤሎሙ ዝንቱ ጽዋዕ ዘሐዲስ ሥርዓት ደምየ ውእቱ ዘይትከዐው በእንቲአክሙ ወበእንተ ብዙኃን ።
ይህ ጽዋ ሐዲስ ሥርዓት የሚሆን ስለናንተ ስለ ብዙ ሰዎችም የሚፈሰው ደሜ ይህ ነው ።

በእንተ ትእምርት ለዘያገብኦ ።

፳፩ ወባሕቱ ናሁ እዴሁ ለዘያገብአኒ ምስሌየ ውስተ ማዕድ ። ማቴ፡፳፮፥፳፩ ማር፡፲፬፥፳ ዮሐ፡ ፲፫ ፥ ፲፰ ።

፳፩ ነገር ግን አሳልፎ የሚሰጠኝ እጅ ከኔ ጋራ በማዕድ ነው ።

፳፪ ወወልደ ዕጓለ እምሕያውሰ የሐውር በከመ ተሠርዓ በእንቲአሁ ። መዝ፡ ፵፥፲ ።

፳፪ የሰው ልጅ ክርስቶስ ግን ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል ።
ወባሕቱ አሌ ሎቱ ለውእቱ ብእሲ እምውስተ እዴሁ ይትሜጠውዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
ነገር ግን አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ ሰው ወዮለት ።

፳፫ ወይቤሉ አርዳኢሁ በበይናቲሆሙ መኑ እንጋ ውእቱ እምኔሆሙ ዘዘንተ ይገብር ።

፳፫ ከርሳቸው ይህን የሚሠራ ማንም እንደ ሆነ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ ።

በእንተ ትሕትና ዘክርስቲያን ።

፳፬ ወእምዝ ተዋከሁ በበይናቲሆሙ እንዘይብሉ መኑ እንጋ የዓቢ እምኔሆሙ ።

፳፬ ከዚህ በኋላ ከርሳቸው ማናቸው እንዲበልጥ እርስ በርሳቸው ተከራከሩ ።

፳፭ ወይቤሎሙ ነገሥቶሙ ለአሕዛብ ይኴንንዎሙ ። ማቴ ፳፥ ፳፭ ማርቆስ ፲፥ ፵፪ ።

፳፭ አሕዛብን ነገሥታቱ ይገዟቸዋል ።
ወመኳንንቲሆሙ ረዳእያነ ይብልዎሙ ።
ገዦቻቸውንም ረዳቶች ይሏቸዋል ።

፳፮ ወለክሙሰ አኮ ከመዝ ።
፳፮ ለናንተ ግን እንዲህ አይደለም
አላ ዘየዓቢ እምኔክሙ ይኩንክሙ ከመ ዘይንእስ።
ከናንተ ታላቁ እንደ ታናሽ ይሁን ።
ወሊቅኒ ከመ ላእክ ።
አለቃውም እንደ ሎሌ ይሁን እንጂ ፤

፳፯ መኑ ውእቱ ዘየዓቢ ።
፳፯ ማን ይበልጣል ።
ዘይረፍቅኑ ።

ተቀምጦ የሚበላው ነውን ።
ወሚመ ዘይትለአክ ፡
ወይም የሚያገለግለው ።
አኮኑ ዘይረፍቅ ።
ተቀምጦ የሚበላው ጌታ ይበልጥ የለምን ።
ወአንሰ ኖሁ ከመ ላእክ ማእከሌሆሙ ።
እነሆ እኔ ዘይረፍቅ እግዚእ ስሆን አገለገልኳችሁ ።

፳፰ ወአንትሙሰ ባሕቲ እለ በእንቲአየ ተዓገሥከሙ ምስሌየ በሕማምየ ።

፳፰ እናንተስ በመከራ ታግሣችሁ ስለኔ መከራዬን የተቀበላችሁ ናችሁ ።

፳፱ አነኒ አሰተዳሉ ለከሙ መንግሥተ በከመ ወሀበኒ ሊተ አቡየ ።

፳፱ አባቴ ለእኔ እንዳዘጋጀ እኔም ለናንተ መንግሥት አዘጋጅላችኋለሁ ። አንድም በነቢይ አድሮ ስአል እምኔየ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ ብሎ እንደ ተናገረልኝ ። ልጅነትን አዘጋጅላችኋለሁ ።

፴ ከመ ትብልዑ ወትሰትዩ በማዕድየ በመንግሥትየ ።

፴ በነገሥኩ ጊዜ በማዕዴ ተቀምጣችሁ ትበሉ ትጠጡ ዘንድ ።
ወትነብሩ ዲበ መናብርት ወትኴንኑ ፲ተ ወ፪ተ ሕዝበ እስራኤል ።
በዐሥራ ሁለት ዙፋን ተቀምጣችሁ ባሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ትፈርዳላችሁ ።

፴፩ ወይቤሎ እግዚእ ለስምዖን ስምዖን ስምዖን ናሁ ስኢለ ሰአሰ ሰይጣን የሐንጽጽከሙ ወየሐንፍጽከሙ ከመ ዐለስ ።

፴፩ ስምዖን ሆይ ሰይጣን እንዳጃ ሲጠረጥራችሁ ከኔ አንድነት ሊለያችሁ ፈጽሞ ተካፈለ ። ሐተታ ደጊመ ቃል ለዕብራውያን ልማዳቸው ነው· አብርሃም አብርሃም ማርታ ማርታ አልዓዛር አልዓዛር እንዳለ ስምዖን ስምዖን አለ ። አንድም ለአጽንዖተ ነገር ። አንድም የነፍስህ የሥጋህ ፈጣሪ ነኝ ሲል ።

፴፪ ወአንሰ ሰአልኩ በእንቲአከሙ ከመ ኢይድክም ሃይማኖትክሙ ።

፴፪ እኔ ግን ሃይማኖታችሁ ሕጹጽ እንዳይሆን ስለናንተ ፈጽሞ ተካሰስኩ ።
ወአንተኒ ተመይጠከ ጽንዖሙ ለአኃዊከ ።
አንተም ከፍርሃት ወደ ጥብዓት ተመልሰህ ወንድሞችህን አጽናቸው ።

፴፫ ወይቤሎ እግዚአ አንሰኬ ጥቡዕ ለሐዊር ። ምስሌከ ውስተ ኢየሩሳሌም እመኒ ተሞቅሐ ወእመኒ ለመዊት ።

፴፫ አቤቱ ኦ እኔስ ለመታሰርም ቢሆን ለሞትም ቢሆን ካንተ ጋር ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቆርጫለሁ ።

፴፬ ወይቤሎ ኦ ጴጥሮስ ዮም ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ሥልሰ ትክሕደኒ ከመ ዘኢተአምረኒ ። ማቴ· ፳፮፡፴፬ ማር. ፲፬፡፴ ።

፴፬ ጴጥሮስ ሆይ ዛሬ ዶሮ ሳይጮህ እንደማታውቀኝ አድርገህ ሦስት ጊዜ ትከደኛለህ ብዬ እነግርሃለሁ ።

፴፭ ወይቤሎሙ አመ ፈነውኩክሙ ዘእንበለ ቍናማት ወጽፍኑት ወአሣዕን ቦኑ ዘተጸነስክሙ ። ማቴ ፲፱፡፴፭ ።

፴፭ ያለ ከረጢት ያለ ስንቅ ያለ ጫማም በላኳችሁ ጊዜ በውኑ የተቸግራችሁት መቸገር አለን በውኑ ተቸገራችሁን አላቸው ።

፴፮ ወይቤልዎ አልቦ ፤
፴፮ አልተቸገርንም አሉት ፤
ወይቤሎሙ ይእዜሰኬ ዘቦ ቍናማት ይንሣእ ሎቱ።
ዛሬ ግን ከረጢት ያለው ይያዝ
ወዘሂ ጽፍነት ፡ ስንቅም ያለው ።
ሐተታ መግቦቱን እስኪያውቁ ድረስ አትያዙ ይላል መግቦቱን ካወቁ በኋላ ግን ቢይዙም ባይዙም አይጐዱምና ።
ወዘሰ አልቦ መጥባሕት ይሢጥ ልብሶ ወይሣየጥ ሎቱ መጥባሐተ ሰይፍ የሌለው ልብሱን ሽጦ በልብሱ ዋጋ ሰይፍ ይግዛ ።
አንድም ፈቃደ ነፍስን ያልያዘ ሰው ፈቃደ ሥጋውን ትቶ ፈቃደ ነፍሱን ይሥራ ።

፴፯ እብለከሙ ከመ ይብጽሐኒ ዘጽሑፍ ወይትፌጸም በላዕሌየ ዘይብል ምስለ ኃጥአን ተኆለቈ ።

፴፯ ከኃጥአን ጋር ተቈጠረ ተብሎ የተነገረው በኔ እንዲደርስ በውነት እነግራችኋለሁ ።
ወኵሉ ዘበእንቲአሃ ይትፌጸም ።
ስለኔ የተነገረው ይፈጸማል ።

፴፰ ወይቤልዎ ነዋ ሀለዉ ኀቤነ ክልኤቱ መጣብሕ ዝየ ።

፴፰ አቤቱ ከዚህ ከኛ ዘንድ እነሆ ሁለት ሰይፎች አሉ አሉት ።
ወይቤሎሙ የአክለነ እንከሰ ።
ሁለት ሰይፍስ ካለ ይበቃናል አላቸው ።
አንድም የአክለከሙ ይበቃችኋል አላቸው ።
አንድም ብሉይንና አዲስን ገንዘብ አድርገናል አሉት ብሉይ ሐዲስ ካያዛችሁስ ይበቃችኋል አላቸው ።

ዘከመ ጸለየ ኢየሱስ በደብረ ዘይት ።

፴፱ ወወፂኦ ሖረ በከመ ያለምድ ይጸሊ ደብረ ዘይት ።

ማቴ፡ ፳፮፡፴፮ ማር፡ ፲፬፡፴፪ ዮሐ፡ ፲፰፡፩ ፡

፴፱ እንደ ለመደ ሊጸልይ ወጥቶ ደብረ ዘይት ሄደ ።
ወተለውዎ አርዳኢሁ ።
ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት ።

፵ ወበጺሖ ህየ ይቤሎሙ ጸልዩ ከመ ኢትባኡ ውስተ መንሱት

፵ ከዚያም በደረሱ ጊዜ ወደ መከራ እንዳትገቡ ጸልዩ አላቸው ።

፵፩ ወተአተተ እምኔሆሙ መጠነ ሙጋረ አብን ወሰገደ ወጸለየ ማቴ፡፳፮፡፴፱ ማር፡ ፲፬፡፴፭ ።

፵፩ የደንጊያ ውርወራ ያህል ማለት ደንጊያ ወርውሮ እስከሚደርስበት ድረስ ከርሳቸው እልፍ ብሎ ሰገደ ጸለየ ።

፵፪ እንዘ ይብል አባ ለእመ ትፈቅድ አግኅሥ እምኔየ ለዝንቱ ጽዋዕ ።

፵፪ አባቴ ሆይ ከወደድህስ ይህን ጽዋዕ ከኔ አርቀው እያለ ።
ወባሕቱ ፈቃድከ ይኩን ወአኮ ፈቃደ ዚአየ ።
ነገር ግን ፈቃድህ ይሁን እንጂ የኔ ፈቃድ አይደለም ።

፵፫ ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ዘይጼንዖ ።

፵፫ ለከ ኃይል ለከ ጽንዕ እያለ የሚያመሰግነው መልአክ ታየው ።
አንድም ዘያጸንዖ የሚያጸናው መልአከ እግዚአብሔር ከወደ ሰማይ ተነጋገረው ።
ወውእቱሰ ፈርሃ ።
እርሱ ግን ፈራ ። ሐተታ በሰው ልማድ ፈራ ፤ ሶበሰ ኢፈርሃ እምኢሰሰለ ፍርሃት እምኔነ ለካሣ ። እንዲል ወአውተረ ጸልዮ ።
መላልሶ ጸለየ ። ወጸርሐ ኀበ አቡሁ ከመ ትምጽእ ረድኤቱ እንዲል ።

፵፬ ወኮነ ሐፉ ከመ ነጸፍጸፈ ደም ዘይወርድ ዲበ ምድር ።

፵፬ ወዙ እንደ ደም ሆነ ማለት በዝቶ ወይቦ ምድሩን አራሰው

፵፭ ወተንሥኦ እምኀበ ይጼሊ ሖረ ኀበ አርዳኢሁ ።

፵፭ ከሚጸልይበት ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሄደ ።
ወረከቦሙ እንዘ ይነውሙ እምኃዘን ።
ከኃዘንም የተነሣ ተኝተው አገኛቸው ።

፵፮ ወይቤሎሙ ምንትኑ ያነውመክሙ ።
፵፮ ምን አስተኛችኋል ።
ተንሥኡ ወጸልዩ ከመ ኢትባኡ ውስተ መንሱት ።
ወደጥፋት እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ አላቸው ።

በእንተ አግብኦት ዘይሁዳ ወተእኅዞት ዘኢየሱስ ።

፵፯ ወእንዘ ዘንተ ይቤሎሙ በጽሐ ሕዝብ።
፵፯ ይህን ሲነግራቸው ሕዝቡ ደረሱ ።
ወይሁዳ ፩ እምዓሠርቱ ወ፪ቱ አርዳኢሁ እንዘ ይመርሆሙ ።
ካሥራሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ይሁዳ እየመራቸው።
ወቀርበ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወሰዓሞ ።
ወደ ጌታ ቀርቦ ሳመው ።
ወዝውእቱ ትእምርት ዘወሀቦሙ ፤
የነገራቸውም ምልክት ይህ ነበርና ።
ወይቤሎሙ ዘሰዓምክዎ ውእቱ ኪያሁ አኀዙ ወሰድዎ አጽኒእኪሙ ።
የምስመው እርሱ ነውና አጽንታችሁ ያዙት አላቸው ።

፵፰ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ለይሁዳ በስኢምኑ ታገብእ ለወልደ ዕጓለ ዕመሕያው ። ማቴ፡ ፳፮ ፵፱ ማር፡ ፲፬፡፵፭ ዮሐ፡ ፲፰፡፫ ።

፵፰ ጌታም ይሁዳ ሆይ የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጠዋለህን ።
አኮኑ ከመ ታቀትሎ ።
ልታስገድለው አይደለምን አለው ።

፵፱ ወርእዮሙ እለ ምስሌሁ ዘኮነ ይቤልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ እግዚኦ ትፈቅድኑ ንዝብጦሙ በመጥባሕት ።

፵፱ ከርሱም ጋራ ያሉት አይተው አቤቱ በሰይፍ ልንገድላቸው ትወዳለህን አሉት ።

፶ ወዘበጦ አሐዱ እምኔሆሙ ለገብረ ሊቀ ካህናት ።

፶ አንዱ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መታው ።
ወመተሮ እዝኖ ዘየማን ።
ቀኝ ጆሮውን ቆረጠው ።

፶፩ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ
፶፩ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ ኅድግ ዘንተ ።
ይህንስ ተው አለው ።
ወገሠሦ እዝኖ ሶቤሃ ።

ያንጊዜውንም ጆሮውን ዳሰ አዳነው ።

፶፪ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእለ መጽኡ፡ ኀቤሁ እምኀበ ያእኀዝዎ ሊቃነ ካህናት ወመገብተ ምኵራብ ወረበናት ከመ ዘሰራቂኑ ተአኃዙኒ መጻእክሙ ምስለ መጣብሕ ወአብትር ፤

፶፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የምኵራብ አዛዦችንና ሊቃነ ካህናትን ሽማግሌዎችን ሌባን እንደምትይዙ በሾተል በጐመድ መጣችሁብኝ አላቸው ።

፶፫ ወእንዘ ሀሎኩ አሚረ ሀሎኩ ምስሌክሙ። ውስተ ምኵራብ እዴክሙ ጥቀ ኢሰፋሕክሙ ላዕሌየ።

፶፫ ዘወትር ከናንተ ጋራ ስኖር እጃችሁን ስንኳ አልዘረጋችሁብኝም ።
ወባሕቱ ዝንቱ ውእቱ ሰዓትክሙ ወሥልጣኑ ለመኰንነ ጽልመት ።
ነገር ግን ጊዜያችሁ ዛሬ ነው የጨለማ አበጋዝ የሚሆን የዲያብሎስም ጊዜው ዛሬ ነው ።

በእንተ ክህደታት ዘጴጥሮስ ።

፶፬ ወአኃዝዎ ወወሰድዎ ቤተ ሊቀ ካህናት ማቴ፡ ፳፮ ፶፯ ፡ ማር፡ ፲፬፡ ፶፫ ።

፶፬ ይዘው ከሊቀ ካህናቱ ቤት ወሰዱት ፤
ወተለዎ ጴጥሮስ እምርኁቅ ።
ጴጥሮስም በሩቅ ተከተለው ።

፶፭ ወአንደዱ እሳተ ማዕከለ ዓጸድ ወነበሩ ። ማቴ፡ ፳፮፡፷፱ ማር፡ ፲፬፡፷፮ ዮሐ፡ ፲፰፡፳፭ ።

፶፭ ባደባባይ መካከል እሳት አንድደው ተቀመጡ ።
ወጴጥሮስኒ ነበረ ምስሌሆሙ
ጴጥሮስም ከርሳቸው ጋራ ተቀመጠ ።

፶፮ ወርእየቶ ወለት እንዘ ይነብር መንገለ በርሀ ።

፶፮ የእሳቱ ጸዳል በወደቀበት በኩል ተቀምጦ ሳለ አንዲት ብላቴና አየችው ።
ወጠየቀቶ ።   አስተዋለች ።
ወትቤዝኒ ምስሌሁ ።
ይህም ከርሱ ጋራ ነበረ አለች ።

፶፯ ወክህደ ወይቤላ አ ብእሲቶ ኢየአምር ዘትብሊ ።

፶፯ አንች ሴት የምትይውን አላውቀውም ብሎ ካደ ።

፶፰ ወእምድኅረ ኅቀ ርእዮ ካልዕ ።
፶፰ ጥቂት ቆይቶም ሌላው አየው ።
ወይቤሎ አንተሂ እምኔሆሙ አንተ ።
አንተም ከርሳቸው ወገን ነህ አለው ።
ወይቤሎ አኀተ ብእሲ ኢኮንኩ አንሰ ።
አንተ ሰው አይደለሁም አለው ።

፶፱ ወኃሊፎ መጠነ አሐቲ ሰዓት አጥዎቀ አሐዱ ካልዕ እንዘ ይብል አማን ዝንቱ ሀሎ ምስሌሁ ዮሐ. ፲፰፡ ፳፮ ።

፶፱ አንድ ሰዓት ከቆየም በኋላም ሌላው ይህም ከርሱ ጋራ ነበር ።
ወገሊላዊ ብእሲ ሁ ።
የገሊላ ሰው ነው ብሎ አስጨነቀው ።

፷ ወይቤሎ ጴጥሮስ አንተ ብእሲ ኢየአምሮ ዘትብል ።

፷ አንተ ሰው የምትለውን አላውቀውም አለ ።
ወእንዘ ውእቱ ይትናገር ዘንተ ነቀወ ዶርሆ ሰቤሃ ።
ይህን ሲናገር ዶሮ ጮኸ ።

፷፩ ወተመይጠ እግዚእነ ኢየሱስ ወነጸሮ ለጴጥሮስ ። ማቴ. ፳፮ ፴፬ ማር፡፲፬፡ ፴ ዮሐ ፲፫ ፡ ፴፰ ።

፷፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ተመልሶ ጴጥሮስን አየው ።
ወተዘከረ ጴጥሮስ ቃሎ ለእግዚእነ ኢየሱስ ዘይቤሎ ሥልሰ ትክህደኒ ዮም ።
ጴጥሮስም ዛሬ ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለውን የጌታን ነገር አሰበ ።
ወወፂአ ጴጥሮስ አፍአ ወበከየ መሪረ ።
ጴጥሮስም ወደውጭ ወጥቶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ ።

ዘከመ ተሣለቁ አይሁድ ላዕለ ኢየሱስ ።

፷፫ ወዕደውኒ እለ አኃዝዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ኮኑ ይሣለቁ ላዕሌሁ ።

፷፫ ጌታን የያዙት ሰዎችም ዘበቱበት ።
፷፬ ይዘብጥዎ ።
፷፬ መቱት ።
ወይገለብብዎ ወይጸፍዕዎ ።
ፊቱን ሸፍነው ጸፉት ።
ወይቤልዎ ተነበይ ለነ መኑ ውእቱ ዘጸፍአከ ወኰርዓከ ።
የመታሕ ማነው ንገረን አሉት ።

፷፭ ወባዕድኒ ብዙኃ ዘይጸርፉ ላዕሌሁ ወይትናገሩ በእንቲአሁ ።
፷፭ ሌላም የሚሰድቡት ብዙ አለ ።

በእንተ ቀዊሞተ ኢየሱስ ውስተ ዓውድ ።

፷፮ ወጸቢሖ ተጋብኡ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት ወሊቃናተ ሕዝብ ወወሰድዎ ውስተ ዓውዶሙ

፷፮ ሲነጋ የካህናቱ አለቆችና ጻሐፊዎች የሕዝቡም አለቆች ተሰብስበው ወዳደባባይ ወሰዱት ።

፷፯ ወይቤልዎ እመ አንተሁ ክርስቶስ ንግረነ ገሃደ ። ማቴ ፳፯ ፩ ማር ፲፭ ፩ ዮሐ ፲፰ ፳፰ ።

፷፯ ክርስቶስ አንተ እንደሆንክ ገልጸህ ንገረን አሉት ።

፷፯ ወይቤሎሙ እይዳዕኩክሙ ፡ ወኢተአምኑኒ ።

፷፯ ብነግራችሁ አትቀበሉኝ ።

፷፰ ወእመኒ ተሰአልኩክሙ ኢትነግሩኒ ወኢታወሥኡኒ ።

፷፰ ብጠይቃችሁ ፡ አትመልሱልኝ ።
ወኢሂ ፡ ኢተኃድጉኒ ።
ወይ አትተውኝ አላቸው ።

፷፱ ወባሕቱ እብለክሙ እምይእዜሰ ትሬእይዎ እንዘ ይነብር ለወልደ ዕጓለ እመሕያው በየማነ እግዚአብሔር ።

፷፱ ነገር ግን ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ከዛሬ ጀምሮ በእግዚአብሔር በቀኙ ኃይል ሲቀመጥ ታዩታላችሁ ።

፸ ወይቤልዎ ኵሎሙ አንተኑ ውእቱ እንከ ወልደ እግዚአብሔር ።

፸ ሁሉም እንኪያ የእግዚአብሔር ልጅ አንተ ነህ አሉት ።

፸፩ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አንትሙ ትብሉ ከመ አነ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ።

፸፩ የእግዚአብሔር ልጅ እኔ እንደሆንኩ እናንተ ትናገራላችሁ ።

፸፪ ወይቤሉ ምንተ እንከ ንፈቅድ ስማዕት በእንቲአሁ ።

፸፪ እንግዲህ ስለ እርሱ ምን ምስክር እንሻለን። ናሁ ለሊነ ሰማዕነ እምአፉሁ ።
እነሆ ካፉ ሰምተናል አሉ ።

በእንተ ቀዊሞተ ፡ ኢየሱስ
ቅድመ ጲላጦስ ወሄሮድስ ።

ምዕራፍ ፳፫ ።

፩ ወተንሥኡ ኵሎሙ በምልኦሙ ወወሰድዎ ኀበ ጲላጦስ ።

፩ ወገኖቻቸው ተነሥተው ወደ ጲላጦስ ወሰዱት ።

፪ ወአኀዙ ያስተዋድይዎ ወይቤሉ ረከብናሁ ለዝንቱ እንዘ የዓልዎሙ ለሕዝብነ ። ማቴ ፳፯ ፡ ፲፩ ማር ፡ ፲፭ ፡ ፪ ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፴፫ ።

፪ ይኸን ሰው ወገኖቻችንን ሲያሳምጽ አገኘነው ብለው ያካስሱት ጀመር ።
ወይከልዎሙ ኢየሀቡ ጸባሕተ ለቄሣር ።
ለቄሣር ግብር እንዳይሰጡ ይከለክላቸዋል ።
ወይሬሲ ርእሶ ክርስቶስሃ ንጉሠ እስራኤል ።
የእስራኤል ንጉሥ ክርስቶስም ነኝ ይላል ብለው አሳጡት ።

፫ ወሐተቶ ጲላጦስ። ማቴ፡፳፯ ፡ ፲፩ ማር ፡ ፲፭ ፡ ፪ ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፴፫ ።

፫ ጲላጦስም መረመረው ።
ወተስእሎ ወይቤሎ አንተኑ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።
የአይሁድ ንጉሣቸው አንተ ነህ ብሎ ጠየቀው ።
ወአውሥአ ወይቤሎ አንተ ትብል ከመ አነ ውእቱ ።
እኔ እንደሆንኩ አንተ ትናገራለህ ብሎ መለሰ ።

፬ ወይቤሎሙ ጲላጦስ ለሊቃነ ካህናት ወለሕዝብ እልቦ ዘረከብኩ አበሳ ላዕለ ዝንቱ ብእሲ ።

፬ ጲላጦስም የካህናት አለቆችና ሕዝቡን በዚህ ሰው ያገኘሁበት በደል የለም አላቸው ።

፭ ወአውየው ወይቤሉ የሀውኮሙ ለሕዝብ ።
፭ ሕዝቡን ያውካቸዋል ያሳዝናቸዋል ብለው ጮኸው ተናገሩ ።
ወይሜህር በኵሉ ይሁዳ እኒዞ እምገሊላ እስከ ዝየ ።
ከገሊላ ጀምሮ እስከዚህ በይሁዳ ሁሉ ያስተምራል ።

፮ ወሰሚዖ ጲላጦስ ስመ ገሊላ ወተስእለ ገሊላውያን ለእመ ገሊላዊ ብእሲሁ ።

፮ ጲላጦስም እኒዞ እምገሊላ ያሉትን ሰምቶ የገሊላ ሰው መሆኑን ጠየቀ ።

፯ ወአእሚሮ ከመ እምኵናነ ሄሮድስ ውእቱ ፈነዎ ኀበ ሄሮድስ ።

፯ ከሄሮድስ ግዛት ወገን እንደሆነ ዐውቆ ወደ ሄሮድስ ላከው ።

እስመ ሀሎ ውእቱ በኢየሩሳሌም በውእቱ መዋዕል ።
እርሱ በዚያ ወራት በኢየሩሳሌም ነበርና ።

፰ ወሶበ ርእዮ ሄሮድስ ለኢየሱስ ተፈሥሐ ፈድፋደ ።

፰ ሄሮድስም ጌታን ባየው ጊዜ ፈጽሞ ደስ አለው ።
እስመ ይፈቅድ ይርአዮ እምጕንዱይ ዐለት ።
ከብዙ ቀን ጀምሮ ሊያየው ይወድ ነበርና ።
እስመ ይሰምዕ ነገሮ ወይሴፎ ይርአይ እምኔሁ ተእምረ ዘይገብር ።

ነገሩን ስለ ሰማ የሚያደርገውን ተአምራት ሊያይ ይመኝ ነበርና ።

፱ ወሐተቶ በብዙኅ ነገር ።
፱ መላልሶ ጠየቀው ።
ወአልቦ ዘተሰጥዎ አሐተ ቃለ ።
አንዲት ቃል ስንኳ አልመለሰለትም ።

፲ ወቆሙ ይቀውሙ ሊቃነ ካህናት ወጸሐፍት።
፲ የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎች ቆመው ነበር።
ወአስተዋደይዎ ብዙኀ ።
አሳጡት ማለት ወዶ ሊመልስልህ አሉት ።

፲፩ ወአስተአከዮ ሄሮድስ ።
፲፩ ሄሮድስም ክፉ ነውሳ አለ ።
ወተሳለቁ ላዕሌሁ ወዓልያኒሁ ።
ብላቴኖቹም ዘበቱበት ።
ወአልበስዎ ልብሰ ቀይሐ ።
የሚብለጨለጭ ልብስ አለበሱት ።
ወፈነዎ ኀበ ጲላጦስ ።
ወደ ጲላጦስም ላከው ።

፲፪ ወይእተ አሚረ ተኳነኑ ሄሮድስ ወጲላጦስ በበይናቲሆሙ ።

፲፪ ሄሮድስና ጲላጦስም ፩ን ጊዜ እርስ በርሳቸው ተፋቀሩ ።
እስመ ጋዕዝቦሙ እምቅድም ።
ከጥንት ጀምሮ ጸብ ነበራቸውና ሐተታ እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በማለት በዳኝነት ምክንያት ፤ አሁን በጌታ ሞት እርቅ እንደተጀመረ ለማጠየቅ ።

፲፫ ወጸውዖሙ ጲላጦስ ለሊቃነ ካህናት ወለመኳንንተ ሕዝብ ።

፲፫ ጲላጦስ የሕዝቡን ገዢዎችና የካህናቱን አለቆች ጠራቸው ።

፲፬ ወይቤሎሙ አምጻእክምዎ ኀቤየ ለዝ ብእሲ ከመ ዓላዌ ሕዝብ ። ዮሐ ፲፰ ፡ ፴፰

፲፬ ሕዝቡን እንደሚያሳምጽ አስመስላችሁ ይህን ሰው ወደኔ አመጣችሁት ።
ወናሁ ሐተትክዎ በቅድሜክሙ ።
እነሆ በፊታችሁ መረመርኩት ።
ወአልቦ ዘረከብኩ ጌጋየ ላዕለ ዝንቱ ብእሲ እምዘ አንትሙ አስተዋደይክምዎ ።
በምታጣሉት ነገር ሁሉ በዚህ ሰው ምክንያት አላገኘሁበትም ።

፲፭ ወኀበ ሄሮድስኒ ፈነውክዎ ።
፲፭ ወደ ሄሮድስም ላክሁት ።
ወውእቱ ፈነዎ ኀቤነ ።
እርሱም ወደኛ ላከው ።
ወናሁ አልቦ ዘገብረ በዘይመውት ።
እነሆ ይሙት በቃ ይፈረድበት ዘንድ በደል አላገኘሁበትም ።

፲፮ እቅሥፎ ወእኅድጎ ።
፲፮ ቀጥቸ ልተወው አለ ።

ዘከመ ኀረዩ በርባንሃ እምነ
ኢየሱስ ወዘከመ ኰነኒዎ ።

፲፯ ወማብር በበዓል ያሕዩ ሎሙ አሐደሙቁሐ እምነ ሙቁሐን ።

፲፯ በየበዓሉ አንዳንድ ሰው ይፈታላቸው ዘንድ ልማድ ነበረ ።

፲፰ ወዓውየው ኵሎሙ ሕዝብ በምልዖሙ ።
፲፰ መላው ጮሁ ።
ወይቤሉ አእትቶ ወስቅሎ ለዝ ።
ይህን አርቀው ሰቀለው ።
ወአሕዩ ለነ በርባንሃ ።
በርባንንም ፍታልን አሉት ።

፲፱ ወውእቱስ በርባን ዘገብረ ሁከከ በውስተ ሀገር ፤ ወበቀቲለ ነፍስ ተሞቅሐ ።

፲፱ ይህም በርባን በሀገር ሁከት ያደረገ ። በነፍስ መግደልም የታሰረ ነበር ።

፳ ወካዕበ ይቤሎሙ ጲላጦስ ትፈቅዱኑ አሕይዎ ለክሙ ለኢየሱስ ።

፳ ዳግመኛም ጲላጦስ ኢየሱስን ላድንላችሁ ትወዳላችሁን አላቸው ።

፳፩ ወአውየው ወይቤሉ ስቅሎ ስቅሎ ።
፳፩ ስቀለው ስቀለው ብለው ጮሁ ።

፳፪ ወይቤሎሙ ጲላጦስ በሣልስ ምንተ እኩየ ገብረ ። ማቴ ፡ ፳ ፡ ፯ - ፳፫ ማር ፲፭ ፡ ፲፬

፳፪ ጲላጦስም በሦስተኛው ምን ክፉ ሥራ ሠራ አላቸው ።
ናሁ አልቦ ዘረከብኩ በላዕሌሁ ጌጋየ በዘይመውት ።
እነሆ የሚሞትበት በደል አላኘሁበትም ።
እቅሥፎኬ እንከ ወአሕይዎ ።
እንግዲህስ ገርፌ ልተወው አለ ።

፳፫ ወአውየው በዐቢይ ቃል ወሰአሉ ወይቤሉ ይሰቅልዎ
፳፫ ስቀለው ብለው ጮኹው ለመኑት ።
፳፬ ወኃየለ ቃሎሙ ወቃለ ሊቃነ ካህናት ።
፳፬ የሊቃናትና የሕዝቡም አለቃ ጩኸታቸው በረታ ጸና ።

ወኰነኖ ጲላጦስ ከመ ይኩኖሙ ፈቃዶሙ ። ጲላጦስም ልመናቸውን ይፈጽምላቸው ዘንድ ፈረደበት ።

፳፭ ወአሕየወ ሎሙ ዘሰአልዎ በቀቲለ ነፍስ ወበገቢረ ሀከክ ተሞቅሐ ።

፳፭ ነፍስ በመግደልና ሁከት በማድረግ የታሰረውን ይፈታላቸው ዘንድ የለመኑትን ፈታላቸው ። ወኢየሱስሃ መጠዎሙ ለፈቃዶሙ በከመ ኀሠሡ ። ኢየሱስን ግን ለፈቃዳቸው ሰጣቸው ።

በእንተ ፍኖት ዘኃዘን ።

፳፮ ወሶበ ወሰድዎ ይስቅልዎ አኃዝዎ ለስምዖን እትወቶ እምሐቅል ። ማቴ ፳፯ ፡ ፴፪ ማር ፲ ፡ ፳ ፳፩ ።

፳፮ ሊሰቅሉት ይዘውት ሲሄዱ ስምዖን የሚባል ሰው ከበረሃ ሲገባ አገኙ ።

፳፮ወአጾርዎ መስቀሎ ወተለዎ ለእግዚእ ኢየሱስ

፳፮ ጌታንም ይከተለው ዘንድ መስቀሉን አሸከሙት ።

ወተለውዎ ብዙኃን ሕዝብ ።
ብዙ ሰዎችም ተከተሉት ።
ወአንስትኒ ይበክያሁ ወያስቆቅዋሁ ።
ሴቶችም ያለቅሱለት ያዝኑለት ነበር ።

፳፰ ወተመይጠ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎን እዋልደ ኢየሩሳሌም ኢትብክያኒ ኪያየሰ ።

፳፰ ጌታም ተመልሶ እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች ለኔስ አታልቅሱልኝ ።
እላ ብክያ ላዕለ ርእስክን ወላዕለ ውሉድክን ።
ለራሳችሁ ለልጆቻችሁ አልቅሱ እንጂ ።

፳፱ እስመ ይመጽእ መዋዕል አመ ይብሉ ብፁዓት መካናት እለ ኢወለዳ ።

፳፱ ያልወለዱ መካኖች የተመሰገኑ ናቸው ።
ወከርሥኒ እንተ ኢወለደት ።
ያልወለደችም ማኅፀን የተመሰገነች ናት ።
ወእጥባት እለ ኢሐፀና ።
ያላጠቡም ጡቶች የተመሰገኑ ናቸው የሚሉበት ጊዜ ይደርሳልና ።

፴ ወይእተ አሚረ ይብልዎሙ ለአድባር ደቁ ላዕሌነ ። ኢሳ. ፪ ፡ ፲፱ ሆሴ ፲፰ ራእ ፮ ፡ ፲፮ ።

፴ ያንጊዜ ተራሮች ወድቀው በተሜኑን ።
ወለአውግርኒ ድፈኑነ ።
ኮረብቶች ተከፍተው ባሰጠሙን ይላሉ ። ሐተታ የመከራውን ጽናት መናገር ነው ሰው መከራ ሲጸናበት ሰማዩ ተንዶ በተጫነኝ ምድር ተከፍቶ ባሰጠመኝ ይላል ።

፴፩ በዝ ዕፅ ርጡብ ከመዝ ዘገብሩ እፎኑመ እንጋ ይከውን በይቡስ ።

፴፩ በዚህ በርጥብ ዕንጨት እንዲህ ያደረጉ በደረቅማ እንዴት ይሆን ማለት ፣ መለኮት በተዋሐደኝ በኔ እንዲህ ያደረጉ እሩቅ ብእሲ ቢያገኙ እንደምን ባደረጉ ። አንድም በኔ እንዲህ ያደረጉ እርሳቸው ለመከራው እንደምን ይስማሙት ይሆን ።

፴፪ ወወሰዱ ካልዓነ ክልኤተ ፈያተ ገባርያነ እከይ ይስቅሉ ።

፴፪ ከርሱም ጋራ ሊሰቅሏቸው ሌሎች ሁለት ወንበዴዎች ወሰዱ ።

በእንተ ተሰቅሎት ኢየሱስ ።

፴፫ ወበጺሖሙ ብሔረ ዘስሙ ቀራንዮ በሀየ ሰቀልዎ ። ማቴ ፡ ፳ ፡ ፯-፴፫ ማር ፡ ፲፭ ፡ ፳፪ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፯-፳ ።

፴፫ ቀራንዮ ከሚባል ቦታም በደረሱ ጊዜ በዚያ ሰቀሉት ።
ወእልክተኒ ክልኤተ ፈያተ ገባርያነ እከይ አሐደ በየማኑ ወአሐደ በጸጋሙ ሰቀሉ ።
እነዚያንም ሁለቱን ወንበዴዎች አንዱን በግራው አንዱን በቀኙ ሰቀሉ ።

፴፬ ወይቤ እግዚእ ኢየሱስ አባ ኅድግ ወስረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ ።

፴፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አባት ሆይ ባላወቁት ይሠራሉና ይቅር በላቸው አለ ። ሐተታ ከዚያ ነቢይ ግፍዖሙ ጽብእሙ እለ ከዚሀ ኅድግሎሙ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ እይጣላም ። ከዚያ የማይመለሱ አሉና ግፍእሙ እያለ ይጸልይባቸዋል ። የሚመለሱ እሉና ከዚህ ስረይ ሎሙ አለ ። ከዚያ እሙንቱሰ ጠይቆሙ ወተዓወሩኒ ይላል ። ከዚህ በዘኢየእምሩ ይገብሩ እለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም እያወቁ ቸል ብለው የሰቀሉት አሉና፣ ነቢይ እሙንቱሰ ጠይቆሙ አለ ሳያውቁ የሰቀሉት አሉና ከዜህ በዘኢየእምሩ ይገብሩ እለ ።
ወተዓፀው ዲበ እልባሲሁ ወተካፈሉ ።
በልብሱ ዕፃ ተጣጥሰው ተካፈሉ ።

፴፭ ወይቀውሙ ሕዝብ ወይሬእዩ ።

፴፭ ሕዝቡም ቆመው ያዩት ነበር ።
ወመላእክትኒ ይዘነጕግዎ ።
አለቆችም ያፌዙበት ነበር ።
ወይቤልዎ ዘባዕደ ያድኀን ርእሶ ያድኅን ።
ሌላውን የምታድን ራስህን አድን ።
እመሰ ክርስቶስ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ወኅሩዩ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር የመረጠው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ከሆንክ ።
ለያድኅን ርእሶ ።
ራሱን ያድን ።

፴፮ ወይሣለቁ ላዕሌሁ ሐራ ወይቀርቡ ።
፴፮ ጭፍሮቹም ቀርበው ይዘብቱበት ነበር ።
ወአምጽኡ ሎቱ ብሒአ ይስተይ ።
መጻጻም አመጡለት ይጠጣ ዘንድ ።

፴፯ ወይቤልዎ እመ ንጉሦሙ ለአይሁድ አድኅን ርእሰከ ።

፴፯ የአይሁድ ንጉሣቸው ከሆንክ ራስክን አድን አሉት ።

፴፰ ወጸሐፉ መጽሐፈ ላዕሌሁ ።
፴፰ ጽሕፈትም በላዩ ጽፈውበት ነበር ።
ወጽሕፈቱ በሮማይስጥ ወበጽርእ ወበዕብራይስጥ ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።
ጽፈቱም በጽርእና በሮማይስጥ በዕብራይስጥ ቋንቋ የአይሁድ ንጉሣቸው ይህ ነው የሚል ነው ።

፴፱ ወአሐዱ ፈያታዊ እም እለ ተሰቅሉ ምስሌሁ ፀረፈ ወይቤሎ እመሰ አንተ ክርስቶስ አድኅን ርእሰከ ወኪያነሂ ።

፴፱ ከርሱ ጋራ ከተሰቀሉት አንዱ ዳክርስ አንተ ክርስቶስ ከሆንክ እኛንም ራስክንም አድን ብሎ ሰደበው ።

፵ ወአውሥኦ ካልኡ ወገሠጾ ።
፵ ሁለተኛውም ተቆጣው ጥጦስ ነው ።
ወይቤሎ ኢትፍርሆኑ ለእግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወአነ እንዘ ውስተ ዝኒቱ ኵነኔ ህለውነ ።
እኔና አንተ በእንደዚህ ያለ ፍርድ ሳለን እግዚአብሔርን አምላክህን አትፈራምን ።

፵፩ ወለነሰ ዘበርቱዕ ረከብነ ዘይደልወነ ።
፵፩ እኛስ በሚገባ ተፈርዶብናል ።
ወበከመ ምግባሪነ ተፈደይነ ።
እንደ ሥራችን ተፈርዶብናል ።
ወዝንቱሰ አልቦ እኩይ ዘገብረ ወኢምንተኒ ።
እርሱ ግን የሠራው ክፉ ሥራ የለም አለው ።

፵፪ ወይቤሎ ለእግዚእ ኢየሱስ ተዘከረኒ እግዚኦ አመ ትመጽእ በመንግሥትከ ።

፵፪ ጌታንም አቤቱ በጌትነትህ በመጣህ ጊዜ በቸርነትህ አስበኝ አለው ።

፵፫ ወአውሥኦ እግዚእ ኢየሱስ ።
፵፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መለሰ ።
ወይቤሎ አማን እብለከ እመን ፈድፋደ ከመ ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት ።
ዛሬ ከኔ ጋራ በገነት እንድትኖር በውነት እነግርሃለሁ አለው ።

በእንተ ገዐሩ ወሞቱ ለኢየሱስ ።

፵፬ ወቀቲሮ ጊዜ ስሱ ሰዓት ሞተ ፀሐይ ።
፵፬ ቀትር ሲሆን በሰድስት ሰዓት ፀሐይ ክብርሃን ተሰየ ።
ወጸልመ ኵሉ ዓለም እስከ ጊዜ ተሱዓት ሰዓት ።
እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ጨለማ ሆነ ።

፵፭ ወጸልመ ፀሐይ ።
፵፭ ፀሐይም ጨለመ ማብራቱን ተወ ። ታሪክ ከቤተልሔም ሲነሡ ሁለት ወንበዴዎች አይተዋቸው ከዱር ሲደርሱ ሊቀሟቸው ተከትለዋቸው ሄዱ ስድስት ቀን ሲፈልጓቸው ሰንብተው በሰባተኛው ቀን አገኙዋቸው ስንፈልጋችሁ ሰንብተን አጥተናችሁ ወዴት ሄዳችሁ ኑሯል ብለው ደብድበው ልብሳቸውን ገፈው ሄዱ ። ከሄዱም በኋላ ጥጦስ ይህች ሴት ከአዝማደ መንግሥት ወገን ናት መሰለኝ አሳዘነችኝ ይህም ሕፃን አሳዘነኝ እንመልስላቸው አለው። ዳክርስ ከሕፃንነትህ ጀምረህ ይህን ያስተማርከን አንተ ነህ ይህን ያህል ርኅራኄ ከማን አገኘኸው በዚያውስ ላይ በማን ፈንታ ታዝለህ አለው ከቤተልሔም እስከዚህ የቀማነው ላንተ ይሁን እኔ በፈንታዬ እቆጠርበታለሁ ተውልኝ ብሎ መለሰላቸው ። ጥጦስ ጌታን ከመቤታችን ተቀብሎ አቀፈው ። አጥጦስ አንተ ትቀድሞ ለአዳም አቡከ በዊአ ውስተ ገነት አለው ። እንዲህ ቢለው ደስ ብሎት ይህ ብላቴና ከደቂቀ ነቢያት ወገን ይመስለኛል አለ ። ዳክርስ ከደቂቀ ነቢያት ወገን ቢሆን ነው አንተን ወንበዴውን ከአዳም አስቀድሞ ገነት ትገባለህ ያለህ ብሎ ዘበተበት ስሎሜም እመቤታችንም ቢሉ ሕፃኑን ተቀብለውት ሲሸኛቸው አንቀፈው ወደቀ ። ሰይፉ ብጥልጥል ብላ ወደቀች አዘነ ሰብስበህ አምጣ አለው እንደ ጥንቱ አድርጎ ሰጥቶታል ከሄዱ በኋላ ለመቤታችን በዕለተ ዓርብ ከኔ ጋራ የሚሰቀሉ እኒህ ናቸው ይህ ያባቱ ፈንታ ነው ያ የዲያብሎስ ፈንታ ነው ብሎ ነግሯቸዋል ።
ወተሠጠ መንጦላዕተ ምኵራብ እማእከሉ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ ።
የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ ።

፵፮ ወጸርሐ እግዚእ ኢየሱስ በዓቢይ ቃል ወይቤ አባ አመሐፅን ነፍስየ ውስተ እዴከ ። መዝ ፴፩ ።

፵፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አባት ሆይ ነፍሴን በጅህ አደራ እሰጣለሁ ብሎ ጮሆ ተናገረ ።

ወዘንተ ብሂሎ መጠወ ነፍሶ ።
ይህንም ተናግሮ ነፍሱን ሰጠ ።

፵፯ ወርእዮ መስፍነ ምእት ዘኮነ አዕኰቶ ለእግዚአብሔር ።

፵፯ የመቶው አለቃም የሆነውን አይቶ እግዚአብሔርን አመሰገነው ።
ወይቤ አማን ጻድቅ ውእቱ ዝንቱ ብእሲ ።
ይህ ሰው በውነት ጻድቅ ኑሯል አለ ።

፵፰ ወኵሎሙ ሕዝብ እለ ኮኑ ጉቡአነ ሶበ ርእዩ ዘኮነ ጐድኡ እንግደዓቲሆሙ ወተሠውጡ ወአተው ቤቶ እንዘ ያነክሩ ።

፵፰ ሕዝቡም ሁሉ የተደረገውን ባዩ ጊዜ ደረታቸውን እየመቱ ተመልሰው ገቡ ። ሐተታ መካነ አንምሮ ነውና ።

፵፱ ወይቀውሙ ኵሎሙ እለ የአምርዎ እምርኁቅ ።

፵፱ የሚያውቁት ሁሉ ርቀው ቆሙ ወአንስትኒ እለ ተለዋሁ እምገሊላ ርእያ ዘንተ ።
ከገሊላ ጀምሮ የተከተሉት ሴቶችም ይህን ያዩ ነበር ።

በእንተ ተቀብሮቱ ለኢየሱስ

፶ ወመጽአ ብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ ።
፶ ዮሴፍ የሚባል ሰው መጣ።
ብእሲ ባዕል ወሥዩም ዘቦቱ ምክር ሠናይ ኄር ።
ማቴ ፣ ፳፯ ፣ ፶፯ ማር ፣ ፲፭ ፣ ፵፫
ቸር ሰው ባለጠጋ ።

ወጻድቅ ፤	ደግ
ወጠቢብ ፤	ዐዋቂ ።

፶፩ ወውእቱ ኢሀሎ ውስተ ምክሮሙ ወምግባሮሙ ለአይሁድ ። ዮሐ ፲፱ ፣ ፴፰ ።

፶፩ እርሱም በአይሁድ ምክርና ሥራ አልተባበረም ነበር ጠቢብ ላለው ።
ወሀገሩ አርማትያስ ዘእምሀገረ ይሁዳ ።
ሀገሩም የዮሁዳ ክፍል የምትሆን አርማትያስ ነበረች ።
ወኮነ ይሴፈዋ ውእቱ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ።
እርሱም መንግሥተ ሰማይን ተስፋ ያደርግ ነበረ ጻድቅ ላለው ።

፶፪ ወሖረ ኀበ ጲላጦስ ወሰአለ ሥጋሁ ለኢየሱስ ።
፶፪ ወደ ጲላጦስም ሄደ የጌታን ሥጋ ላውርድ ብሎ ለመነ ኄር ላለው ።

፶፫ ወአውረደ ሥጋሁ ወገነዞ በሰንዱናት ።
፶፫ ሥጋውን አውርዶ በድርብ በፍታ ከፈነው ባዕል ላለው ።
ወቀበሮ ውስተ መቃብር ሐዲስ ዘውቅሮዝ አውቀረ ዘአልቦ ተቀብረ ውስቴቱ ።
እሱ ባሳነጸው ሰው ባልተቀበረበት በታነጸ መቃብርም ቀበረው ።
ወአንኰርኰረ እብነ ዓቢየ ወአንበረ ውስተ አፈ መቃብር ወኃለፈ ።
ታላቅ ደንጊያ አንላብጦ መቃብሩን ገጥሞት ሄደ ።

፶፬ ወዓርብ ውእቱ ዕለት አሚሁ ለጸቢሐ ሰንበት ።

፶፬ ያም ቀን የሰንበት አጥቢያ ዓርብ ነበር ።
፶፭ ወተለዋሁ ፪ቲ አንስት እለ መጽአ እምገሊላ ።

፶፭ ከገሊላ የመጡ ሁለት ሴቶችም ተከትለውታል ።
ወርእያ መቃብሮ ወዘከመ ተወድየ ሥጋሁ ።
መቃብሩንም አዩ ሥጋው እንዴትም እንደ ተጨመረ ።
ወእምድኅረ ቀበርዎ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ሥጋውንም ከቀበሩት በኋላ ፤

፶፮ ወአተዋ ወአስተዳለዋ አፈዋተ ።
፶፮ ተመልሰውም ሽቱ አዘጋጁ ።
ወኃደጋ በሰንበት ወኢሖራ ።
በሰንበት ግን አልሄዱም ።
እስመ ከማሁ ሕጎሙ ።
ሕጋቸው እንዲህ ነበርና ።

በእንተ ተንሥኦቱ ለኢየሱስ

ምዕራፍ ፳፬

፩ ወበእሑድ ሰንበት በጽባሕ አሌለያ ገይሥ ወሖራ ኀበ መቃብር ወወሰዳ ውእተ አፈዋተ ዘአስተዳለዋ ። ማቴ ፣ ፳፰ ፣ ፩ ማር ፣ ፲፮ ፣ ፪፡ዮሐ ፣ ፳ ፣ ፩ ።

፩ በመጀመሪያው ሰንበት ማለዳ ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው እጅግ ማልደው ወደ መቃብር ሄዱ።
ወካልዓትኒ አንስት ምስሌሆን ።
ሌሎችንም ሴቶች ከርሳቸው ጋራ ሄዱ ።

፪ ወረከባሃ ለይእቲ እብን ኀበ አንኰርኰረት እምነ መቃብር ።

፪ ያችንም ደንጊያ ከመቃብሩ ተነሥታ አገኙዋት ።

፫ ወቦአ ወኢረከባ ሥጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ።
፫ ገብተውም የጌታችንን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም ።

፬ ወእንዘ ያንከራ ወየኃጥአ በእንተ ዝንቱ ።

፬ ስለዚህም ነገር የሚሉትን አጥተው ሲያደንቁ ።
አስተርአይዎን ፪ቱ እደው ወቆሙ ኀቤሆን ።
ሁለት ሰዎች ባጠገባቸው ቁመው ታዩዋቸው ።
ወይበርቅ አልባሲሆሙ ።
የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ነበር ። ወርኃ ትፍሥሕት ነው ሲሉ ።

፭ ወፈርሃ ወአትሐታ አዕይንቲሆን ውስተ ምድር ።

፭ ፈርተውም ዓይናቸውን ወደ ምድር ዝቅ አድርገው አዩ ።
ወይቤልዎን ምንተ ተኃሥሣሁ ለሕያው ምስለ ምውታን ።
ሕያውን ከሙታን ጋራ ለምን ትሹታላችሁ ።

፮ ተንሥአ ኢሀሎ ዝየሰ ። ማቴ ፲፯ ፥ ፳፩ ማር ፰ ፥ ፴፩ ሉቃ ፱ ፥ ፳፪

፮ ከዚህ ግን የለም ተነሥቷል ።

፯ ተዘከራ ቃሎ ዘይቤለክን በገሊላ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለእመሕያው ይግባእ ውስተ እደ ሰብአ ኃጥአን ።

፯ በገሊላ ሳለ ለሰው ልጅ ክርስቶስ በኃጥአን እጅ ይሰጥ ዘንድ አለው ።
ወይሰቅልዎ ፤　　ይሰቅሉታል ።
ወይቀትልዎ ፤　　ይገድሉታል ።
ወይትነሣእ በሣልስት ዕለት ።
በሦስተኛው ቀን ይነሣል ያላችሁን አስቡ አሏቸው ።

፰ ወተዘከራ ቃሎ ።

፰ ነገሩንም አሰቡ ።

፱ ወአቲዎን እምኀበ መቃብር ነገራሆሙ ዘንተ ለ፲፩ቱ ወ፩ዱ አርዳኢሁ ።

፱ ከመቃብሩም ተመልሰው ለዐሥራ አንዱ ነገሩዋቸው ።
ወለቢጾሙኒ ኵሎሙ እለ ተርፉ ።
ለቀሩት ባልንጀሮቻቸውም ሁሉ ።

፲ ወእማንቱሰ ማርያም መግደላዊት ወዮሐና ።

፲ እርሳቸውም የመግደላዊቱ ማርያምና ዮሐና ናቸው ።
ወማርያም እንተ ያዕቆብ ።
የያዕቆብ እናት ማርያምም ናት ።
ወቢጽንሂ ምስሌሆን ነገራሆሙ ዘንተ ለሐዋርያት ።
ከርሳቸውም ጋራ ያሉ ባልንጀሮቻቸው ይህን ለሐዋርያት ነገሩዋቸው ።

፲፩ ወኮነ ዝንቱ ነገር ዘሰምዑ በቅድሜሆሙ ከመ ዝኒጋዔ ።

፲፩ የዝንጋታ መስሏቸው ማለት አእምሮ የማጣት መስሏቸው ።

፲፪ ወኢአምንዎን ፤

፲፪ አልተቀበሏቸውም ።
ወአክሐድዎን ፤
አሉ አሏቸው ሐሰት አሏቸው ።
ወተንሥአ ጴጥሮስ ወሮጸ ወሖረ ኀበ መቃብር ።
ጴጥሮስም ተነሥቶ ወደመቃብር ሮጦ ሄደ ።
ወሐወጸ ፤　　ዘልቆ ተመለከተ ።
ወርእየ መዋጥሐ ባሕቲቶ ንቡረ ።
በፍታወንም ብቻውን ተቀምጦ አየ ።
ወአተወ እንዘ ያነክር ዘኮነ ፤
የተደረገውን እያደነቀ ተመለሰ ።

በእንተ አርድዕት ዘኤማሑስ ።

፲፫ ወይእተ ዕለተ እንዘ የሐውሩ ፪ቱ እምውስቴቶሙ ሀገረ እንተ ርኁቅት እምኢየሩሳሌም መጠነ ፷ ምዕራፍ እንተ ስማ ኤማሑስ ። ማር ፲፮ ፥ ፲፪።

፲፫ በዚያን ቀን ከርሳቸው ሁለቱ ከኢየሩሳሌም ስሳ ምዕራፍ ያህል የሚርቅ ኤማሑስ ወደ ምትባል አገር ሲሄዱ ፤ ሐተታ ፪ቱ ያላቸው ሉቃስና ቀለዮጳ ናቸው። ሉቃስንስ ዘውእቱ ቀለዮጳ ይሉዋል ብሎ ሉቃስና ኒቆዲሞስ ናቸው ።

፲፬ ወይትናገሩ በበይናቲሆሙ በእንተ ኵሉ ዘኮነ ።

፲፬ ስለተደረገውም ነገር ሁሉ ሲጫወቱ ።

፲፭ ወእንዘ እሙንቱ ይትናገሩ ወይትኃሠሥዎ፥ ለዝንቱ ።

፲፭ ይህን ሲነጋገሩ ሲመራመሩ ።
ቀርቦሙ እግዚእ ኢየሱስ ወሖረ ምስሌሆሙ ።
ጌታችን ኢየሱስም ቀርቦ ከርሳቸው ጋራ ሄደ ።

፲፮ ወተእኅዘ አዕይንቲሆሙ ከመ ኢያእምርዎ።

፲፮ እንዳያውቁት ዓይናቸው ከዕውቀት ተገታ።

፲፯ ወይቤሎሙ እግዚእነ ምንትኑ ዝንቱ ነገር ዘትትናገሩ በበይናቲክሙ እንዘ ተሐውሩ ትኩዛኒክሙ ።

፲፯ እያዘናችሁ ስትሄዱ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩት ይህ ነገር ምንድነው አላቸው ።

፲፰ ወአውሥአ ፩ዱ እምኔሆሙ ዘስሙ ቀለዮጳ ።

፲፰ ከርሳቸው አንዱ ቀለዮጳ የሚባለው መለሰ።
ወይቤሎ አንተኑ ባሕቲትከ ነግድ ዘኢሀለውከ በኢየሩሳሌም ።
አንተ ብቻህን በኢየሩሳሌም አልነበርህምን ?

ወኢያእመርከኑ ዘኮነ በውስቴታ በዝንቱ መዋዕል ።
በዚህ ወራት በርሷ የተደረገውን አላወቅህምን አለው

፲፱ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ምንትኑ ውእቱ
፲፱ ጌታም ምንድነው አለው ።
ወይቤልዎ በእንተ ኢየሱስ ናዝራዊ ።
የናዝሬቱን የኢየሱስን ነገር ይነግሩት ጀመር ።
ብእሲ ጻድቅ ፤ ደግ ሰው ።
ወነቢይ ፤ ዐዋቂ የሆነ ።
ዘኮነ ከሃሌ በቃሉ ወበምግባሩ በቅድመ እግዚአ
ብሔር ወበቅድመ ሰብእ ።
በተናገረው ነገር በሚሠራው ሥራ በእግዚአብሔር
ዘንድ በሰውም ዘንድ ማድረግ የሚቻለው ።

፳ ወዘከመ አግብእዎ ሊቃነ ካህናት ወመ
ኳንንቲነ ።

፳ የካህናት አለቆችና አለቆቻችን አሳልፈው
እንደሰጡት ።
ወኰነንዎ ለሞት ።
ለሞት ፍርድ አሳልፈው ሰጡት ።
ወሰቀልዎ ፤ ሰቀሉት ።

፳፩ ወንሕነሰ ነአምን ቦቱ ከመ ውእቱ ሀለዎ
ያድኅኖሙ ለእስራኤል ።

፳፩ እኛ ግን እርሱ እስራኤልን ያድናቸው
ዘንድ እንዳለው እናምናለን ።
ወምስለ ዝንቱ ኵሉ ሠሉስ ዮም እምዘኮነ ዝንቱ ።
ከዚህም ሁሉ ጋራ ይህ ከተደረገ ዛሬ ሦስተኛ ቀን
ነው ።

፳፪ ወቦ አንስትኒ እለ አንከራ ወነገራነ እለ
ጌሣ ኀበ መቃብር ወኢረከባ ሥጋሁ ።

፳፪ ወደ መቃብር ገሥግሠው ሂደው ሥጋ
ውን ባያገኙ አድንቀው የነገሩን ሴቶች አሉ ።

፳፫ ወተሠውጣ ወነገራነ ከመ ርእያ ርእየተ
መላእክት እለ ይቤልዎን በእንቲአሁ ከመ ሐይወ ።

፳፫ ተመልሰውም እንደ ዳነ የነገሩዋቸውን
የመላእክትን መልክ እንዳዩ ነገሩን ።

፳፬ ወቦ እምኔነሂ እለ ሖሩ ኀበ መቃብር ወረ
ከባ ከማሁ በከመ ይቤላ አንስት ።

፳፬ ከኛም ወገን ወደ መቃብር የሄዱ ሴቶች
እንዳሉት ሆኖ ያገኙት አሉ ።
ወሎቱሰ ኢረከብዎ ።
እርሱን ግን አላገኙትም ።

፳፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ዓብዳን
ወጉንዱያነ ልብ ለኢአሚን በኵሉ ዘይቤሉ ነቢያት ።

፳፭ ነቢያት በተናገሩት ነገር ሁሉ ልቡናችሁ
ከማመን የዘገየ እናንት ያላስተዋላችሁ ።

፳፮ አኮኑ ከመዝ ጽሑፍ ከመ ሀለዎ ለክርስ
ቶስ ከመ ይትቀተል ወይባእ ውስተ ስብሐቲሁ ።

፳፮ ክርስቶስ መከራ ይቀበል ዘንድ ወደክ
ብሩም ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን ።

፳፯ ወአኀዘ ይፈክር ሎሙ እምነ ሙሴ ወዘ
ነቢያት ።

፳፯ ከኦሪት ከመጻሕፍተ ነቢያት እየጠቀሰ ።
ወእምኵሉ መጻሕፍት ዘበእንቲአሁ ።
ስለ እርሱ የተጻፉ ስለ ርሱ የሚናገሩ መጻሕፍትን
እየጠቀሰ እየተረጐመ ይነግራቸው ጀመር ።

፳፰ ወቀርቡ ሀገረ ኀበ የሐውሩ ባቲ ።
፳፰ ወደሚሄዱበት አገር ወደኤማሁስ ቀረቡ ።
ወአኀዘ ይትረኃቆሙ ።
ይርቃቸው ጀመር ።

፳፱ ወአገበርዎ ወይቤልዎ ንበር ምስሌነ ።

፳፱ ግድ ከኛ ጋራ እደር ብለው ማለዱት ።
እስመ መስየ ወተቆልቆለ ፀሐይ ።
መሽቶ ፀሐይ ገብቷልና ።
ወቦአ ከመ ይኅድር ምስሌሆሙ ።
ከርሳቸውም ጋራ ሊያድር ገባ ።

፴ ወእምዝ እንዘ ይረፍቅ ምስሌሆሙ ነሥአ
ኅብስተ ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ።

፴ ከርሳቸው ጋራም ተቀምጦ ሲበላ ዳቦውን
ይዞ ጸሎተ ማዕድ ጸልዮ ቆርሶ ሰጣቸው ።

፴፩ ወተከሥታ አዕይንቲሆሙ ።
፴፩ አእምሮዋቸው ተገለጠላቸው ።
ወአእመርዎ ፤ ዓወቁት ።
ወጠፍአ ፤ ነገሩን አጡት ።
ወእምዝ ተሰወረ እምኔሆሙ ፡ ተሰወረባቸው ።
ወኃጥእዎ ፤ እንዳላወቁት ሆኑ ።

፴፪ ወይቤሉ በበይናቲሆሙ አኮኑ ይነድደነ
ልብነ ።

፴፪ እርስ በርሳቸው እንዲህ አሉ ልቡናችን
ያዝን ይጸጸት የለምን ።
ወይረኅቀነ እንዘ ይነግረነ በፍኖት ።
በመንገድ እየነገረን ሲርቀን ።
ወይፌክር ለነ መጻሕፍተ ።
መጻሕፍትን ሲተረጕምልን አናውቅ ብለን ።

፴፫ ወተንሥኡ ሶቤሃ ይእተ ሰዓተ ወተሠ
ውጡ ኢየሩሳሌም ።

፴፫ በዚያን ሰዓት ፈጥነው ወደኢየሩሳሌም
ተመለሱ ።
ወረከብዎሙ ለ፲ ወ፩ዱ አርዳኢሁ ጉቡአኒሆሙ ።

ዐሥራ አንዱን ሐዋርያት ተሰብስበው አገኙዋቸው ።
ወለእለሂ ምስሌሆሙ ።
ከርሳቸው ጋራ ያሉትን ።

፴፬ ወይቤልዎሙ አማን ተንሥአ እግዚእነ ወአስተርአዮ ለስምዖን ።

፴፬ ጌታችን በውነት ተነሥቶ ለስምዖን ታየው ።
፴፭ ወነገርዎሙ እሙንቱሂ ዘበፍኖት ።
፴፭ እርሳቸውም በመንገድ የሆነውን ነገሯቸው ።
ወዘከመሂ አእመርዎ ለእግዚእነ እንዘ ይፌትት ኅብስተ ።
ጌታንም ዳቦውን ሲቆርስ እንዳወቁት ።

፴፮ ወእንዘ ዘንተ ይትናገሩ ቆመ እግዚእ ኢየሱስ ማእከሎሙ ።
ወይቤሎሙ ሰላም ለከሙ ። ማር ፲፮ ፡ ፲፬ ዮሐ ፳፡ ፲፱

፴፮ ይኸንም ሲናገሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዝግ ቤት ገብቶ በመካከላቸው ቆሞ እንደምን ሰነበታችሁ አስታረቅኋችሁ ።
ወኢትፍርሁ አነ ውእቱ ።
እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው ።

፴፯ ወደንገፁ ወፈርሁ ወመሰሎሙ ከመ ዘመንፈሰ ይሬእዩ ።

፴፯ እርሳቸው ግን ምትሐት ያዩ መስሏቸው ። ምትሐት እንዳዩ አድርገው ፈሩ ደነገጡ ።

፴፰ ወይቤሎሙ ምንት ያደነግፀክሙ ።
፴፰ ጌታም አላቸው ለምን ትደነግጣላችሁ ።
ወለምንት የዐርግ ሕሊና እኩይ ውስተ ልብክሙ ።
በልባችሁስ ክፉ አሳብ ለምን ይወጣል ይወርዳል ።

፴፱ ርእዩ እደውየ ወእገርየ ከመ አነ ውእቱ ወእእምሩኒ ።

፴፱ እጄን እግሬን አይታችሁ እኔ እንደሆንኩ ዕወቁ ።
እስመ ለመንፈስሰ ሥጋ ወዓፅም አልቦቱ በከመ ትሬእዩኒ ብየ ።

በኔ እንደምታዩት ለምትሐት ሥጋ ዓፅም የለውምና፤ ሐተታ በነፍስ መደብ ሆኖ ብየ አለ ለኔ ግን ሥጋ ዓፅም አለኝ ማለቱ ነው ።

፵ ወዘንተ ብሂሎ አርአዮሙ እደዊሁ ወእገሪሁ ።

፵ ይኸን ተናግሮ በችንካር የተወጋውን እጁን እግሩን አሳያቸው ።

፵፩ ወእንዘ ዓዲ ኢአምኑ እምድንጋጼ ።
፵፩ ከድንጋጼ የተነሣ ገና ሳያምኑ ፤
ወእንዘ ያነክሩ በትፍሥሕት ።
ደስ ብሏቸውም ሲያደንቁ ።
ይቤሎሙ ደቂቅየ ቦኑ ብክሙ ዝየ ዘንበልዕ ።
ልጆቼ የምንበላው አላችሁ አላቸው ።

፵፪ ወወሀብዎ መክፈልተ ዓሣ ጥቡስ ።
፵፪ የተጠበሰ ዓሣ ፤
ወጸቃውዓ መዓር ።
ሰፈፍ የሌለው ወለላ ማር ሰጡት ።

፵፫ ወበልዓ በቅድሜሆሙ ።
፵፫ በፊታቸው በላ ። ሐተታ ለልማዱ ሲመገብ ስድስቱ ይቆማሉ ስድስቱ ይቀመጣሉ በዚህ ቀን ግን ዐሥራ አንዱ እንደ ቆሙ ተመግበዋል ። ትንሣኤውን እንዲረዱት ምትሐት እንዳይደለ ለማጠየቅ ።
ወነሥአ ዘተርፈ ወወሀቦሙ ።
የተረፈውን አንሥቶ ሰጣቸው ።

፵፬ ወይቤሎሙ አኮኑ ዝንቱ ነገርየ ዘአቤለከሙ እንዘ ሀሎኩ ምስሌክሙ ።

፵፬ ከናንተ ጋራ ሳለሁ የነገርኋችሁ ነገሬ ይህ አይደለምን ።
ከመ ሀለዎ ይብጻሕ ኦሪተ ሙሴ ወነቢያት ወመዝሙር በእንቲአየ ።
ኦሪት ነቢያት ዳዊት ስለኔ የተናገሩት ነገር ይደርስ ዘንድ እንዳለው ።

፵፭ ወእምዝ ከሠተ ልቦሙ ከመ ይለብዉ መጻሕፍተ ።

፵፭ ከዚህ በኋላ መጻሕፍትን ያውቁ ዘንድ አእምሯቸውን ገለጠላቸው ።
ወለበዉ ፤ ዓወቁ ።
ወሶበ ተንሥአ እምነ ምውታን ከሠተ ሎሙ መጻሕፍተ ወለበዉ ወኮኑ ከመ ሰብል እንዲል ።

፵፮ ወይቤሎሙ ከማሁ ጽሑፍ ከመ ይትቀተል ክርስቶስ ወይትነሣእ እምውታን በሣልስት ዕለት

፵፮ ክርስቶስ እንዲሞት በሦስተኛውም ቀን ከሙታን እንዲነሣ እንዲሁም ተጽፏል ብሎ ነገራቸው ።

፵፯ ወይሰብኩ በስሙ ለንስሐ ።
፵፯ ስሙ ሕይወት መድኃኒት እንደሆነ ሲያምኑ ወለኅድገተ ኃጢአት ።
ኃጢአት ሊሰረይ ያስተምሩ ፤
ወለኵሉ ሕዝብ እኒዞሙ እምኢየሩሳሌም ።
ከኢየሩሳሌም ጀምረው ለሕዝቡ ሁሉ ሊያስተምሩ ።

፵፰ ወአንትሙሰ ሰማዕቱ ለዝንቱ ነገር ።
፵፰ እናንተም ለዚህ ነገር ምስክሮች ናችሁ ።
፵፱ ወናሁ እፌኑ ተስፋሁ ለአቡየ ላዕሌክሙ ። ዮሐ ፲፬ ፡ ፳፮ ።

፵፱ እኔም እስውጥ እምነ መንፈስየ ዲበ ኵሉ ዘሥጋ ብሎ ያናገረውን ተስፋ መንፈስ ቅዱስን እሰድላችኋለሁ ።

ወአንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ።
እናንተ ግን ከሰማይ ኃይል እስክትለብሱ ማለት ሰማያዊ ሀብትን ሰማያዊ ዕውቀትን ገንዘብ እስክ ታደርጉ ድረስ በኢየሩሳሌም ኑሩ ።

፶ ወእምዝ አውፅኦሙ አፍአ እስከ ቢታንያ ወአንሥአ እደዊሁ ላዕሌሆሙ ወባረኮሙ ።

፶ ወደ አፍአ እስከ ቢታንያ ድረስ አውጥቶ በአንብሮተ እድ እስከ ፓትርያርክነት ያለውን ማዕ ርግ ሾማቸው ።

፶፩ ወእንዘ ይባርኮሙ ተረኃቆሙ ወዓርገ ሰማየ ። ማር. ፲፮ ፡ ፲፱ ግብ/ ሐ. ፩ ፡ ፱ ።

፶፩ ሾሟቸው የርቀት ያይደለ የርኅቀት ተሰ ውሯቸው ወደ ሰማይ ዓረገ ።

፶፪ ወእሙንቱሰ ሰገዱ ሎቱ ወተሠውጡ ኢየ ሩሳሌም በዓቢይ ፍሥሐ ።

፶፪ እርሳቸው ግን ደስ ብሏቸው እጅ ነሥተው ሰግደው ኢየሩሳሌም ተመለሱ ።

፶፫ ወነበሩ በቤተ መቅደስ እንዘ ዘልፈ ይባ ርክዎ ለእግዚአብሔር ።

፶፫ ዘወትር እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑት ሲያገለግሉ በቤተ መቅደስ ኖሩ ።
መልአ ጽሕፈተ ብሥራቱ ስሉቃስ ወንጌላዊ አሐዱ እምሰብአ ወክልኤቱ አርድዕት ዘጸሐፎ በልሳነ ዮናኒ ለሰብአ ሀገረ መቄዶንያ እምድኅረ ዕርገቱ ለእግዚእነ ውስተ ሰማይ በዕሥራ ወአሐዱ ዓመት ወበ፲ቱ ወ፩ቱ ዓመተ መንግሥቱ ለአቅሎንድዮን ቄሣር ።

ከሰባ ሁለቱ አርድእት አንዱ ሉቃስ አቅሎንድዮስ ቀላውዲዎስ ቄሣር በነገሠ በሀሥራ አራት ዓመት ጌታችን ወደ ሰማይ ባረገ በሃያ አንድ ዓመት ለመቄዶንያ ሰዎች በዮናኒ ቋንቋ የጻፈው ወንጌል ደረሰ ተፈጸመ ።
ወስብሐት ለእግዚአብሐር ።
አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለእግዚአብሔር ክብር ምስ ጋና ይግባው ። አሜን ።

◆

ትልቁ ምዕራፍ ዐቢይ ዘወንጌለ ሉቃስ ።	የሉቃስ ወንጌል የዐቢይ ምዕራፍ ቍጥር ።
ምዕራፍ ፩ እስመ ብዙኃን እለ አኀዙ ።	ወንጌልን ሊጽፉ የዠመሩ ብዙ ናቸውና ።
ም ፪ ። ወኮነ በውእቱ መዋዕል ወፅአ ትእዛዝ	በዚያ ወራት ትእዛዙ ወጣ ።
ም ፫ ። ወአመ ዐሠርቱ ወኃምስቱ ።	በዐሥራ አምስተኛው ።
ም ፬ ። ወመልአ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኢየሱስ ።	በጌታ መንፈስ ቅዱስ መላ ።
ም ፭ ። ወሀለዉ ሰብእ ብዙኃን ።	ብዙ ሰዎች ነበሩ ።
ም ፮ ። ወእምዝ ካዕበ ወፈረ እግዚእ ኢየሱስ ።	ዳግመኛ ጌታ ሔደ ።
ም ፯ ። ወፈጺሞ ነጊሮቶሙ ቃሎ ለሕዝብ ።	ለሕዝብ አስተምሮ ከጨረሰ በኋላ ።
ም ፰ ። ወእምዝ በሳኒታ አንሶሰወ ውስተ አህጉር	ከዚህ በኋላ በነጋው ባውራጃው ሁሉ ተመላለሰ ።
ም ፱ ። ወጸውዖሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ሐዋርያት ።	ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ጠራቸው ።
ም ፲ ። ወእምዝ አርአየ ካልኣነ ሰብአ ።	ከዚህ በኋላ ሌሎች ሰብዓን መረጠ ።
ም ፲፩ ። ወእምዝ ጸለየ በአሐቲ መካን ።	ከዚህ በኋላ ባንዲት ቦታ ጸለየ ።
ም ፲፪ ። ወተጋብኡ ኀቤሁ አእላፍ ሰብእ ።	ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ ።
ም ፲፫ ። ወቦ እለ መጽኡ ኀቤሁ አሚሃ ።	ያንጊዜ ወደሱ የመጡ ሰዎች አሉ ።
ም ፲፬ ። ወእምዝ ሖረ ወኮነ ሶበ በጽሐ ።	ከዚህ በኋላ ሔዶ በደረሰም ጊዜ ።
ም ፲፭ ። ወሀለዉ ይቀርብዎ መጸብሐን ።	መጸብሐን ይቀርቡት ነበሩ ።
ም ፲፮ ። ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ	ጌታ ለተማሪዎቹ እንዲህ አላቸው ።
ም ፲፯ ። ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ግብር ይመጽእ መንሱት ።	ለተማሪዎቹ ግድ ጥፋት ይመጣል አላቸው ።
ም ፲፰ ። ወይቤሎሙ በምሳሌ ከመ ዘልፈ ይጸልዩ።	ዘወትር እንዲጸልዩ በምሳሌ ነገራቸው ።
ም ፲፱ ። ወበዊአ ኢያሪሆ አንሶሰወ ።	ኢያሪሖ በገባ ጊዜ ተመላለሰ ።
ም ፳ ። ወእምዝ አሐተ ዕለተ እንዘ ይሜህሮሙ	ከዚህ በኋላ አንድ ቀን ሲያስተምራቸው ።
ም ፳፩ ። ወነጸረ ወርእየ አብዕልተ ዘከመ ያበውኡ መባዓ ።	መባ የሚያገቡትን ባለጠጎች አየ ።
ም ፳፪ ። ወቀርበ በዓለ መጸለት ።	የቂጣ በዓል ቀረበ ።
ም ፳፫ ። ወተንሥኡ ኵሎሙ በምልአሙ ።	ሁሉም በመላው ተነሡ ።
ም ፳፬ ። ወበእሑድ ሰንበት በጽባሕ ።	እሑድ ማለዳ ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌል ሉቃስ ።		የሉቃስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
እስመ ብዙኃን እለ አኀዙ ይጽሐፉ ፤	ምዕ ፩ ቍ ፩	ወንጌልን ሊጽፉ የጀመሩ ብዙ ናቸውና ።
በእንተ ዘከመ አይድዓ ገብርኤል መልአክ ልደቶ ለዮሐንስ ፤	ቍ ፭	ገብርኤል የዮሐንስን ልደት እንደ ተናገረ ።
በእንተ ዘከመ አብሠራ ለማርያም ሥጋዌሁ ለቃል	ቍ ፳፮	የጌታን ሰው መሆን ለማርያም እንደ ነገራት ።
በእንተ ብጽሐት ኀበ ኤልሳቤጥ	ቍ ፴፱	ወደ ኤልሳቤጥ እመቤታችን እንደ ደረሰች ።
በእንተ ልደተ ዮሐንስ መጥምቅ ፤	ቍ ፶፯	ስለ ዮሐንስ መወለድ ።
በእንተ ልደተ ኢየሱስ ፤	ም ፪ ቍ ፩	ስለ ኢየሱስ መወለድ ።
በእንተ ዘከመ ተገዝረ ኢየሱስ ወዘከመ አቀምዎ ውስተ ቤተ መቅደስ ፤	ቍ ፳፩	ስለ ጌታ መገዘርና ከቤተ መቅደስ ውስጥ ስለ አቆሙት ።
በእንተ ኢየሱስ ሕፃን	ቍ ፴፱	ስለ ሕፃን ኢየሱስ ።
በእንተ ዘከመ ረፈቀ ኢየሱስ ማእከለ ሊቃውንት	ቍ ፵፩	ስለ ጌታ መቀመጥ ከሽማግሎች መካከል ።
በእንተ ስብከት ዘዮሐንስ መጥምቅ ፤	ም ፫ ቍ ፩	ስለ ዮሐንስ ማስተማር ።
በእንተ ዘከመ ተሞቅሐ ዮሐንስ መጥምቅ	ቍ ፲፱	ስለ ዮሐንስ መታሰር ።
በእንተ ጥምቀቱ ለኢየሱስ ፤	ቍ ፳፩	ስለ ጌታ መጠመቅ ።
በእንተ መጽሐፈ ትውልድ ዘኢየሱስ ፤	ቍ ፳፫	ስለ ጌታ ትውልድ ቍጥር ።
በእንተ ተመክሮት ዘኢየሱስ	ም ፬ ቍ ፩	ስለ ጌታ መፈተን ።
በእንተ ዘከመ አኀዘ ኢየሱስ ይስብክ በገሊላ።	ቍ ፲፬	ስለ ጌታ ማስተማር በገሊላ ።
በእንተ ዘከመ ሰበከ ኢየሱስ በናዝሬት ።	ቍ ፲፮	ስለ ጌታ ማስተማር በናዝሬት ።
በእንተ ዘከመ ኀደጋ ኢየሱስ ለናዝሬት ወዘከመ ሖረ ቅፍርናሆም ።	ቍ ፴፩	ጌታ ናዝሬትን ስለ ተዋት ፤ ወደ ቅፍርናሆምም ስለሔደ ።
በእንተ ዘከመ አሕየወ ኢየሱስ ዘቦቱ ጋኔን ።	ቍ ፵፫	ጌታ ጋኔን ያደረበትን ስለ አዳነ ።
በእንተ ዘከመ አሕየዎሙ ኢየሱስ ለሐማተ ጴጥሮስ ወለካልዓን ሕሙማን ።	ቍ ፴፰	ጌታ የጴጥሮስን አማትና ፤ ሌሎች በሽተኞችን ስለ አዳነ ።
በእንተ ዘከመ አኀዙ በተአምር ብዙኃ ዓሣ ።	ምዕራፍ ፭ ቍ ፩	ብዙ ዓሣን በታምራት ስለ ያዙ ።
በእንተ ተጸውዖቶሙ ለሐዋርያት ቀዳማውያን ።	ቍ ፱	የቀደሙ ሐዋርያት ስለ ተጠሩ ።
በእንተ ዘከመ አሕየዎሙ ኢየሱስ ለለ ምጻዊ ወለመፃጉዕ ።	ቍ ፲፪	ጌታ ለምጻሙንና መፃጉዕን ስለ አዳነ ።
በእንተ ተኀርዮተ ሌዊ ።	ቍ ፳፯	ስለ ሌዊ መመረጥ ።
በእንተ ጾም ዘክርስቲያን ።	ቍ ፴፫	ስለ ክርስቲያን ጾም ።
በእንተ ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ በእንተ ሰዊት ወዕለተ ሰንበት ።	ም ፮ ቍ ፩	ጌታ ስለ እሸትና ስለ ሰንበት እንደ ተናገረ ።
በእንተ ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ ለዘየብሰት እዴሁ ።	ቍ ፮	ጌታ እጁ የደረቀችውን ስለ አዳነው ።
በእንተ ዘከመ ሰመዮሙ ለ፲ቱ ወ፪ቱ ሐዋርያት ።	ቍ ፲፪	ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት እንደ ሾማቸው ።

መክሥተ ርእስት ዘወንጌለ ሉቃስ ።		የሉቃስ ወንጌል ርእስት ማውጫ ።
በእንተ ስብከት በውስተ ደብር ወበእንተ ብፁዓን ።	ቍ ፳	በተራራ ስለ አስተማረና ስለ ብፁዓን ሰዎች ።
በእንተ ሐዲስ ኪዳን አስተናጽሮታ ምስለ ብሊት ።	ቍ ፴፮	አዲስ ሕግንና ብሊት ሕግን ስለ ማነጻጸር ።
በእንተ ካልዓን ትእዛዛት ።	ቍ ፴፱	ስለ ሌሎች ትእዛዛት ።
በእንተ ወዒሊ ዘመስፍን ።	ም ፯ ቍ ፩	ስለ ሹም ባሪያ ።
በእንተ ዘከመ አንሥአ ለወልደ መበለት ።	ቍ ፲፩	የባልቴቱን ልጅ ስለ አነሣው ።
በእንተ ኢየሱስ ወበእንተ አርድእተ ዮሐንስ መጥምቅ ።	ቍ ፲፰	ስለ ጌታና ስለ ዮሐንስ ተማሪዎች ።
በእንተ ዘከመ ወደሶ ኢየሱስ ለዮሐንስ መጥምቅ ።	ቍ ፳፬	ጌታ ዮሐንስን ስለ አመሰገነው ፤
በእንተ ፈሪሳዊ ወኃጥእት ብእሲት ።	ቍ ፴፮	ስለ ኃጥእት ሴትና ስለ ፈሪሳዊ ፤
በእንተ ዘከመ ዖደ ኢየሱስ አኅጉረ ገሊላ ።	ም ፰ ቍ ፩	ጌታ በገሊላ አውራጃ ስለ ዞረ ።
በእንተ ምሳሌ ዘዘራዒ ።	ቍ ፬	ስለ ገበሬው ምሳሌ ።
በእንተ አዝማዲሁ ለኢየሱስ ።	ቍ ፲፱	ስለ ጌታ ዘመዶች ።
በእንተ ኅድዓተ ባሕር ።	ቍ ፳፪	ስለ ባሕር ጸጥታ ፤
በእንተ ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ ለዘቦቱ ጋኔን በብሔረ ጌርጌሴኖን	ቍ ፳፮	ጌታ ጋኔን ያደረበትን በጌርጌሴኖን ስለ አዳነው ።
በእንተ ወለተ ኢያዒሮስ ወበእንተ ደም ይውኅዛ ።	ምዕራፍ ፰ ቍጥር ፵	ስለ ኢያዒሮስ ልጅና ደም ስለሚፈሳት ።
በእንተ ዘከመ መሀሮሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት ወበእንተ ተፈንዎቶሙ ።	ም ፱ ቍ ፩	ጌታ ሐዋርያትን ስለ አስተማራቸውና ስለመላካቸው።
በእንተ ሐልዮተ ሄሮድስ ላዕለ ኢየሱስ ።	ቍ ፯	በጌታ ላይ ሄሮድስ ስለአሰበ ፤
በእንተ ተመይጦተ ዘሐዋርያት ፤	ቍ ፲	ስለ ሐዋርያት መመለስ ፤
በእንተ ብዝኃተ ኅብስት ቀዳማይ ፤	ቍ ፲፪	መጀመሪያ እንጀራ ስለአበረከተ ፤
በእንተ እምነተ ጴጥሮስ ወበእንተ ትንቢተ ዘሕማማት ።	ቍ ፲፰	ስለ ጴጥሮስ ማመን ስለጌታ መከራ መናገር ፤
በእንተ ክሂደ ርእሱ ለክርስቲያን ፤	ቍ ፳፫	ክርስቲያን ሰው ራሱን ስለ መካድ ።
በእንተ ተወልጦተ ራእዩ ለኢየሱስ ።	ቍ ፳፰	የጌታ መልኩ ስለመለወጥ ።
በእንተ ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ ለዘያንገረግሮ ጋኔን	ቍ ፴፯	ጌታ ጋኔን የሚጥለውን ስለ አዳነው ።
በእንተ ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ እቅድሙ ነገረ ሞቱ ።	ቍ ፵፬	ጌታ አስቀድሞ የሞቱን ነገር ስለተናገረ ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ትሕትና ወተዓግሦተ ቢጽ ።	ቍ ፵፮	ለክርስቲያን ወንድሙን መታገሥና ትሕትና ስለ ሚገባው ።
በእንተ ዘከመ ተሰደ ኢየሱስ እምሰማርያ ።	ቍ ፶፩	ጌታ ከሰማርያ ስለ ሄደ ።
በእንተ ዘከመ ይደሉ በተሊወተ ኢየሱስ ፤	ቍ ፶፯	ጌታን በማናቸውም መከተል እንዲገባ ።
በእንተ ተፈንዎት ለሐዋርያት ቀዳማውያን ።	ም ፲ ቍ ፩	ስለ ሐዋርያት መላክ ።
በእንተ ዘከመ ተመይጡ እምዘተፈነዉ ።	ቍ ፲፯	ሐዋርያት ከተላኩበት ስለተመለሱ ።
በእንተ ድኅነት ።	ቍ ፳፩	ስለ መዳን ።

መክሥተ እርእስት ዘወንጌለ ሉቃስ ።		የሉቃስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ተራኅርኆተ ሳምራዊ	ቍ ፳፭	ስለ ሳምራዊ መራራት ማዘን ።
በእንተ ማርያ ወማርታ ።	ቍ ፴፰	ስለ ማርያና ማርታ ።
በእንተ ጸሎት ክርስቲያናዊት ።	ም ፲፩ ቍ ፩	ስለ ክርስቲያን ጸሎት ።
በእንተ ጽሙም ዘአኃዞ ጋኔን	ቍ ፲፬	ጋኔን ስለያዘው ደንቆሮ ።
በእንተ መናፍስት እኩያን ።	ቍ ፳፬	ስለ ክፉዎች አጋንንት ።
በእንተ ዘከመ ብፁዕ ውእቱ ዘይሰምዕ ቃለ እግዚእብሔር ።	ምዕራፍ: ፲፩ ቍ ፳፯	ወንጌልን የሚሰማ ብፁዕ እንደሆነ ።
በእንተ ትእምርተ ዮናስ ።	ቍ ፳፱	ስለ ዮናስ ምልክት ።
በእንተ ኢየሱስ ወፈሪሳውያን	ቍ ፴፯	ስለ ጌታና ስለ ፈሪሳውያን ።
በእንተ ብጉዕ ዘፈሪሳውያን ።	ም ፲፪ ቍ ፩	ስለ ፈሪሳውያን እርሾ ።
በእንተ ትዝሕርት ወበእንተ እኩይ ባዕል፣	ቍ ፲፫	ስለ ትዕቢትና ስለክፉ ባለጠጋ ።
በእንተ ዘከመ ኢይደልዎ ለክርስቲያን ተፀዕቦት በከንቱ ።	ቍ ፳፪	ለክርስቲያን በከንቱ መቸገር እንዳይገባ ።
በእንተ ተጊሆት ።	ቍ ፴፭	ስለ መትጋት ።
በእንተ ዕርቅ ።	ቍ ፶፰	ስለ ዕርቅ ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ገቢረ ንስሐ በዞርሕ ።	ም ፲፫ ቍ ፩	ለክርስቲያን በግድ ንስሐ እንዲገባው ።
በእንተ በለስ ዘእልባቲ ፍሬ ።	ቍ ፮	ፍሬ ስለሌላት በለለ ።
በእንተ ብእሲት ዘድኅነት እምደዌሃ በዕለተ ሰንበት ።	ቍ ፲	በሰንበት ከደዌዋ ስለዳነች ሴት ።
በእንተ ኅጠተ ስናፔ ወበእንተ ብጉዕ ።	ቍ ፲፰	ስለ ሰናፍጭ ቅንጣትና ስለ እርሾ ።
በእንተ ጉልቄ ኅሩያን ።	ቍ ፳፫	ስለ ተመረጡ ቍጥር ።
በእንተ ጽልዕ ዘሄሮድስ ።	ቍ ፴፩	ስለ ሄሮድስ ጥል ።
በእንተ ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ ተኀድጎታ ለኢየሩሴም ።	ቍ ፴፬	ጌታ ኢየሩሳሌም እንድትቀር እንደተናገረ ።
በእንተ ዘከመ ፈወሶ ኢየሱስ ለቅብው በሰንበት ።	ም ፲፬ ቍ ፩	ጌታ በሰንበት ሆዱ ያበጠውን ስለ ፈወሰው ።
በእንተ ዘከመ መሀረ ኢየሱስ ትሕትና ወፍቅረ ለእለ ይረፍቁ ።	ቍ ፯	ጌታ ለተቀመጡ ትሕትናንና ፍቅርን ስለአስተማረ ።
በእንተ ምሳሌ ዘዕሡራን ።	ቍ ፲፮	ስለ ተቀጠሩ ሰዎች ምሳሌ ።
በእንተ ዘከመ ይደሉ ተሊዎተ ኢየሱስ ።	ቍ ፳፭	ጌታን ስለ መከተል ።
በእንተ ተገድፎተ በግዕ ፤	ም ፲፭ ቍ ፩	ስለ በግ ጥፋት
በእንተ ተረክቦተ ገመስ ።	ቍ ፰	ስለ ቀለበት መገኘት ።
በእንተ ተኀጕሎቱ ወተመይጦቱ ለወልድ ፤	ቍ ፲፩	ስለ ልጅ መጥፋትና መመለስ ።
በእንተ መጋቢ ዘኢይትአመን	ም ፲፮ ቍ ፩	ስለ የማይታመን ሹም ።
በእንተ ተመድልዎት ዘፈሪሳውያን ።	ም ፲፮ ቍ ፲፬	ስለ ፈሪሳውያን ግብዝነት ።
በእንተ ባዕል ።	ቍ ፲፱	ስለ ባለጠጋው ፤
በእንተ ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ ባዕለ ዕቅፍት ።	ም ፲፯ ቍ ፩	ስለ መጠራጠር እንደተናገረ ፤
በእንተ ገሥጾተ አኃው ።	ቍ ፫	ስለ ወንድሞች ምክር ።
በእንተ ኃይል ዘሃይማኖት ወዘከመ ይደሉ ፈጽሞቱ ለግብር ።	ቍ ፭	ስለ ሃይማኖት ኃይል ስለ ሥራ መፈጸም ።
በእንተ ፲ቱ እለ ለምጽ ።	ቍ ፲፩	ስለ ዐሥሩ ለምጻሞች ።

መክሥተ እርእስት ዘወንጌለ ሉቃስ ።	የሉቃስ ወንጌል እርእስት ማውጫ ።
በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር ወበእንተ ተመይጦቱ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ። ቍ ፳	ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ ክርስቶስ መምጣት ።
በእንተ መኰንን እኩይ ። ምዕ ፲፰ ቍ ፩	ስለ ክፉ ሹም ።
በእንተ ፈሪሳዊ ወመጸብሐዊ ። ቍ ፱	ስለፈሪሳዊና ስለ መጸብሐዊ ።
በእንተ ኢየሱስ ወሕፃናት ፤ ቍ ፲፭	ስለ ጌታና ስለ ሕፃናት ልጆች ።
በእንተ ወሬዛ ባዕል ፤ ቍ ፲፰	ስለ ጐልማሳ ባለጠጋ ።
በእንተ ተላውያነ ኢየሱስ ፤ ቍ ፳፰	ጌታን ስለሚከተሉ ።
በእንተ ትንቢት ዘሕማማት ፤ ቍ ፴፩	ስለ መከራው መናገር ።
በእንተ ዕውር ዘኢያሪሆ ። ቍ ፴፭	ስለ ኢያሪሆ ዕውር ።
በእንተ ዘኬዎስ መጸብሐዊ ምዕ ፲፱ ቍ ፩	ስለ ዘኬዎስ ።
በእንተ ምሳሌ ዘምናናት ፤ ቍ ፲፩	ስለ ወርቅ ምሳሌ ።
በእንተ በዓተ ኢየሩሳሌም ዘኢየሱስ ቍ ፳፰	ስለ ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት ።
በእንተ ተሰዶቶሙ ለእለ ያረኩሱ ቤተ መቅደስ ። ቍ ፵፭	ቤተ መቅደስን የሚያረክሱ ስለ መስደድ ፤
ዘከመ ተስእሎሙ ኢየሱስ ጥምቀተ ዮሐንስ ምዕ ፳ ቍ ፩	የዮሐንስን ማስተማር ስለ ጠየቃቸው ፤
በእንተ እኩያን ዓቀብተ ወይን ፤ ቍ ፱	ስለ ክፉዎች ወይን ጠባቂዎች ።
በእንተ ጸባሕት ዘቄሣር ፤ ቍ ፲፱	ስለ ቄሣር ግብር ።
በእንተ ሰዱቃውያን ወትንሣኤ ሙታን ፤ ቍ ፳፯	ስለ ሰዱቃውያንና ስለሙታን መነሣት ።
በእንተ ዘከመ ውእቱ መሲሕ ወልደ ዳዊት ። ቍ ፵፩	ስለ መሲሕ የዳዊት ልጅ ።
በእንተ ተመድልዎት ዘጸሐፍት ፤ ቍ ፵፭	ስለ ጸሐፊዎች ግብዝነት ።
በእንተ ጸሪቀ መበለት ንዳይት ፤ ምዕ ፳፩ ቍ ፩	ስለ ድሀይቱ እንጀራ ።
በእንተ ትንቢት ዘጥፍእተ ቤተ መቅደስ ወሀገረ ኢየሩሳሌም ። ቍ ፭	ስለ ኢየሩሳሌምና ስለቤተ መቅደስ ጥፋት መናገር ።
በእንተ ዘከመ በዓይ ጥፋእታ ለኢየሩሳሌም ወሕዝብ ምዕራፍ ፳፩ ቍጥር ፳	የኢየሩሳሌም ጥፋት በማናቸውም ስለሆነ ።
በእንተ እለ ይቀድሙ ትእምርታት ዘዕለተ ደይን ወደ ኅሪት ምጽአቱ ለኢየሱስ ። ቍ ፳፭	ስለ ሚቀድሙ የፍርድ ቀን ምልክቶችና ፤ ስለ ጌታ በኋላ መምጣት ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ተደልዎት ለምጽአተ ኢየሱስ ኰናኒ ። ቍ ፳፱	ጌታ ለሚመጣበት መዘጋጀት እንዲገባ ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎ ለክርስቲያን ተደልዎ ለሞት ። ቍ ፴፬	ክርስቲያን ሰው ለሞት መዘጋጀት እንዲገባው ።
በእንተ ምክር ዘረ ወ፪ቱ ፈታሕያን ላዕለ ኢየሱስ ። ምዕ ፳፪ ቍ ፩	ስለ ሰባ ሁለቱ ፈራጆች ምክር ።
በእንተ ተሰናዕዎቱ ለይሁዳ ምስለ አይሁድ። ቍ ፫	ስለ ይሁዳ ከአይሁድ ጋራ መስማማት ።
በእንተ ደኅሪት ድራር ወአስተዳልዎት ። ቍ ፯	ስለ ኋለኛይቱ እራት ማዘጋጀት ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌል ሉቃስ ።		የሉቃስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ሠሪዖተ ቍርባን ቅዱስ ።	ቍ ፲፱	ስለ ቅዱስ ቍርባን ።
በእንተ ትእምርት ለዘያገብኦ ፤	ቍ ፳፩	ስለ ሚያሲዘው ይሁዳ ምልክት ።
በእንተ ትሕትና ዘክርስቲያን ።	ቍ ፳፬	ስለ ክርስቲያን ትሕትና ።
በእንተ ዘከመ ጸለየ ኢየሱስ በደብረ ዘይት ።	ቍ ፴፱	ስለ ጌታ ጸሎት በደብረ ዘይት ።
በእንተ እግብኦት ዘይሁዳ ወተእኅዞቱ ለኢየሱስ ።	ቍ ፵፯	ስለ ይሁዳ መስጠትና ስለ ጌታ መያዝ ።
በእንተ ክህደት ዘጴጥሮስ ።	ቍ ፶፩	ስለ ጴጥሮስ መካድ ።
በእንተ ዘከመ ተማለቁ እይሁድ ሳዕለ ኢየሱስ ፤	ቍ ፷፫	ስለ አይሁድ በጌታ መዘበት ።
በእንተ ቀዊሞተ ኢየሱስ በውስተ ዐውድ ።	ቍ ፷፮	ስለ ጌታ በሸንጎ መቆም ።
በእንተ ቀዊሞተ ኢየሱስ ቅድመ ጲላጦስ ወሄሮድስ ም. ፳፫	ቍ ፩	ስለ ጌታ መቆም በጲላጦስና በሄሮድስ ፊት ።
በእንተ ዘከመ ኀረዩ በርባንሃ እምነ ኢየሱስ ወዘከመ ኰነንዎ ፤	ቍ ፲፮	ስለ በርባን መመረጥና ስለ ጌታ መፈረድ ።
በእንተ ፍኖት ዘኀዘን ፤	ቍ ፳፮	ስለ ኀዘን መንገድ ።
በእንተ ተሰቅሎተ ኢየሱስ ፤	ቍ ፴፫	ስለ ጌታ መሰቀል ።
በእንተ ጸዐሩ ወሞቱ ለኢየሱስ ።	ቍ ፵፬	ስለ ጌታ መጮህና ሞት ፤
በእንተ ተቀብሮቱ ለኢየሱስ ፤	ቍ ፶	ስለ ጌታ መቀበር ፤
በእንተ ተንሥኦቱ ለኢየሱስ ፤ ም ፳፬	ቍ ፩	ስለ ጌታ መነሣት ፤
በእንተ እርድእት ዘኤማኁስ ፤	ቍ ፲፫	ስለ ኤማኁስ ተማሪዎች ፤
በእንተ ዘከመ አስተርአዮሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት ።	ቍ ፴፮	ስለ ጌታ መታየት ለሐዋርያት ።
በእንተ ዘከመ ዐርገ ኢየሱስ ውስተ ሰማይ ።	ቍ ፶፩	ስለ ጌታ ወደ ሰማይ መውጣት ፤

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል ።
ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ጻፈው ።

ብሥራት አብ ትሩፍ ረድዕ ተናጋሪ በመለኮት ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ፍቁረ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

> ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ይህ ቃል የሠለስቱ ምእት ነው ጥንተ ነገሩ እንደምን ነው ቢሉ እንደ ማቴዎስ ተርከ ዮሐንስ እንዳባቶቹ እንደ ነቢያት እንደ ወንድሞቹ እንደ ሐዋርያት አይጽፍም ። አባቶቹ ነቢያት በሥነ ፍጥረት በዋዌ ባገባብ ይጀምራሉ ፣ በሥነ ፍጥረት በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ብለው ባገባብ አኮኑ አንተ ትቤ እመ ፈጠርካሃ ለምድር ብለው በዋዌ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ ብሔረ አውሲጢድ ዘስሙ ኢዮብ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ በብሔረ አርማቴም እምደብረ ኤፍሬም ዘመሴፋ ዘስሙ ሕልቃና ። ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ በብሔረ ባቢሎን ዘስሙ ኤልያቄም ብለው እንዳባቶቹ እንደ ነቢያትስ ይሁን ። እንደ ወንድሞቹ እንደ ሐዋርያት አለመጻፉ ስለምን ነው ቢሉ ፣ እንደ ማቴዎስ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም ብሎ ከአብርሃም ከዳዊት መወለዱን ተናግሮ ቢሆን ከዳዊት ከአብርሃም የተወለዱ ብዙ ነገሥታት አሉ የኒያ ይብቃው ባሉት ነበርና ። እንደ ማርቆስ ወልድየ አንተ ብሎ የባሕርይ ልጅነቱን ቢናገር ።

እስራኤል ወልድየ ዘበኵርየ ይባላሉ በጸጋ የሚወለዱ የምእመናን ልደት ይብቃው ባሉት ነበርና እንደ ሉቃስ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላእሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ብሎ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና መወለዱን ቢናገር አዳም ቅሉ ከኅቱም ምድር ተገኝቶ የለምን የርሱ ይብቃው ባሉት ነበርና ፣ መስተጻርር መስተቃርን የሌለበት ደረቅ ቃል ቀዳሚሁ ቃል አለ ይህን አርእስት ፫ቱ ምእት ሰጥተዋል ፣ እንደ ማቴዎስ ተርከ ብሥራት ማቴዎስብሥራት ማርቆስብሥራት ሉቃስ፣ብሥራት እብ ትሩፍ ረድዕ ተናጋሪ በመለኮት ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ፍቁረ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እያሉ ስለምን ነው ቢሉ ጥንቱን የጻሐፈው ደግነት የታወቀ እንደሆነ የመጽሐፉም ደግነት ይታወቃልና ይደልዎ ለዘያነብብ ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዓለ መጽሐፍ ወእምዝ ያንብብ ወይምሐር እንዲል ። ወንጌል ስብከት ብሥራት ቢል አንድ ነው ። ወንጌል ብሂል በልሳነ ጽርእ ወትርጓሜሁ ስብከት እንዲል፣ ዲያብሎስ እንደተሻረ ወልደ እግዚአብሔር እንደ ነገሠ ። ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደጠፋ ትናገራለችና ። አብ አለ በትምህርት ይወልደናልና እስመ አነ ወለድኩክሙ በትምህርት ክርስቶስ እንዲል፣ ትሩፍ አለ ። በክብርም በግብርም ፍጹም ነውና ረድዕ አለ ። መጠኑ ለረድ እምከመ ኮነ ክመ ሊቁ ያለው የተፈጸመለት ክርሱ በቀር ሌላ የለምና ተናጋሪ በመለኮት መለኮተ ሲል ነው ። በግእዝ የገባ ነው ፣ ወአንተሰ ኢቀባዕከኒ በዘይት ርእስየ እንዲል ። ያንድነትን የሦስትነትን ነገር የተናገረ ፣ አንድም እንዳለው ተናጋሪ በመለኮት። በመለኮት ድሕንፃ ተቃኝቶ ያንድነትን የሦስትነትን ነገር የተናገረ ፣ በዚህ ታዮኅሎስ ተብሏል ። ነባቤ መለኮት ማለት ነው ። ጎርጎርዮስ ምሥጢረ ሥላሴን እምልቶ አስፍቶ አብዝቶ ቢናገር ነባቤ መለኮት እንደ ተባለ። ልመናው ከብሩ ይደርብንና የዘብዴዎስ ልጁ የክርስቶስ ወዳጁ ካሥራ ሁለቱ ሐዋርያት እንዱ ዮሐንስ የተናገረው ወንጌል ስብከት ብሥራት ብትል ይህ ነው ፍቁረ እግዚእነን ፫ቱ ፻ት ከራሳቸው አንቅተው አልተናገሩትም ከወንጌል ከውስጡ ረድዕ ዘያፈቅሮ ያለውን አግኝተው ተናግረውታል እንጂ

በእንተ ክዊኖቱ ለቃል መለኮታዊ ወቀፈንዎቱ ለዮሐንስ ።

ምዕራፍ ፩ ።

፩ ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ።

ጌታ ወንጌላውያንን ሲያጽፍ በመዋቅር ጀመረ በመሠረት ጨረሰ ነገር ግን ቤት ከመዋቅሩ እስከ መሠረቱ ከመሠረቱ እስከ መዋቅሩ የተያያዘ ነው እንጂ የተለያየ አይደለም ተጠመቀ ለማለት ተወለደ ማለት ጥንቱ ነው ። ተወለደ ለማለት ተፀነሰ ማለት ጥንቱ ነው ። ተፀነሰ ለማለት በቅድምና ነበረ ማለት ጥንቱ ነው ።

፩ ያቃል በቅድምና የነበረ ነው ወእንተሰ ጥበብ እምላዕሉ ቀዳሚሃ ንጽሕት ይእቲ ወሰውእቱ

መቅድመ ቃል ይባርከዎ እንዲል የት ተናግሮት ነበርና ውእቱ ብሎ አጻፈ ቢሉ ከወንድሞቹ አያይዞ፥ እንደ ወንድሞቹስ አይጽፍም ብለናል ብሎ በጥንተ ስብከት ላስተማራቸው ውእቱ ብሎ አጻፈላቸው በጥንተ ስብከት ያስተማርኳችሁ ያ ቃል በቅድምና የነበረ ነው ። እንድም ቀዳሚሁ ለፍጥረት ለየ ቀረው ነው ከሥነ ፍጥረት አስቀድሞ የነበረ ነው አእትሪኮን በርፎሪኮን አተርግዋን የሚባሉ ዝርዋን ቃላት እሉ ቃለ ሰብእ ቃለ እንስሳ ቃለ መላእክት

ስለ ሦስት ነገር ቃል ብሎታል ህልውናቸውን ቅድምናቸውን ለመናገር ፈጠረበትም ለማለት ህልውናቸውን ለመናገር ከልብ ከትንፋሽ ተለይቶ በአፍአ የሚገኝ ቃል የለም ። ህልዋን እሙንቱ በአብ እንዘ ይሄልዉ በበ አካላቲሆሙ ነአምን በአብ ከመ ህልው በወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወነአምን በወልድ ከመ ህልው በአብ ወመንፈስ ቅዱስ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ከመ ህልው በአብ ወወልድ እንዲል ቀድምናቸውን ለመናገር ። ልብ እስትንፋስ ቀድመው ወደኋላ የሚገኝ ቃል የለም ፡ አሐቲ ቅድምና ሆሙ ለሥላሴ ወዕሩያን እሙንቱ በቅድምና እንዲል ። ፈጠረበትም ለማለት አብኒ ፈጠረ በቃሉ ዘውእቱ እምነ መለኮቱ ወኵሎ ፈጠርከ በቃልከ እንዲል ። አምላክ ወልድ አይለውምን ቢሉ አምላክ ቢለው እንስ እቤ አማልክት አንትሙ ያላቸው እሉ የኒያ ይብቃው ባሉት ነበርና ። ወልድም ቢለው እሥራኤል ወልድየ ዘበኵርየ ይባላሉ ምእመናን በጸጋ የሚወለዱት ልደት እለ የነዚያ ይብቃውባሉት ነበርና ዳግመኛም ወልድ ብሎት ቢሆን የሁለቱን አንድነት ነው እንጂ የሦስቱን አንድነት አያስረዳምና ወዝስም ዘውእቱ ወልድ ያጤይቅ ኅብረተ ህላዌሆሙ ለአብ ወለወልድ እንዲል ። ቃል ግን የሦስቱን አንድነት ያስረዳልና ቃለ አብ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ ወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ እንዲል ያውስ ቢሆን የሦስቱን አንድነት በሚያስረዳ እዱ መዝራዕቱ የማኑ አይለውምን ቢሉ የአፍአ አንድነታቸውን ነው እንጂ የውስጥ አንድነታቸውን አያስረዳምና ውሳጣዊ አንድነታቸውን በሚያስረዳ ጥበቡ ምክሩ ሕሊናሁ አይለውምን ቢሉ የምክር የሕሊና መዲናቸው መገለጫቸው ቃል ነውና በመዲናቸው በመገለጫቸው በቃል ተናገረው እንድም ቃል ከልብ ተገኝቶ በልብ ህልው ሁኖ ሲኖር ልገለጽ ባለ ጊዜ ባንደበት እንዲገለጽ እርሱም ከአብ ተገኝቶ በአብ ህልው ሆኖ ሲኖር ልገለጽ ባለ ጊዜ በሥጋ ተገልጧልና ዳግመኛ ለምሳሌ ይመቸኝ ብሎ ለቃል እርምሞ ጽርአት የለውም በልቡና ሲወጣ ሲወርድ ይኖራል ጸሐፊ ቀለም በጥብጦ ብርዕ ቀርጾ ብራና ደምጦ በጸፈ ጊዜ ረቂቁ ቃል ከልቡና ሳይለይ በቀለም ገዝፎ እንዲታይ ረቂቅ አካላዊ ቃልም ከአብ አንድነት ሳይለይ በሥጋ ገዝፎ ታይቷልና በዚህም ቃል ኃደረ በብእሲ የሚል ሳምሳጢ ጳውሎስ ሰፈ አማርያም የሚሉ አለፎጢኖስ ተረተውበታል ።

ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ። በቅድምናም ነበረ ያልሁት ያ ቃል በእግዚአብሔር አብ ህልው ነው ጸዳል በከበብ ነበልባል በእሳት ርጥበት በስፍሐት ቃል በልብ ህልው ሁኖ እንዲኖር ህልዋን እሙንቱ በአብ እንዘ ይሄልዉ በበአካላቲሆሙ ነአምን በአብ ከመ ህልው በወልድ መንፈስ ቅዱስ። ወነአምን በወልድ ከመ ህልው በአብ ወመንፈስ ቅዱስ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ከመ ህልው በአብ ወወልድ እንዲል ። በዚህም ቃል መዓርገ መንግሥት የሚሰጡ እለ አቡሊናርዮስ መዓርገ ርቀት የሚሰጡ እለ አርጌንስ አንድ ገጽ የሚል ሰባልዮስ ተረተውበታል ። ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል ፥ ያቃል እግ እግዚአብሔር ነው ማለት ጸዳል በከበብ ርጥበት በስፍሐት ነበልባል በእሳት ቃል በልብ ህልው ሆኖ እንዲኖር አይደለም ። በተለየ አካሉ ፈጥር የሚገዛ ነው ። ይህስ እንዳይሆን ለምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ ነው ምሳሌ ያፈርሳል ብሎ ደቀ መዝሙር ከመምህሩ ሎሌ ከጌታው ተጠግቶ እንደሚገዛው አገዛዝ ያይደለ በተለየ አካሉ ፈጥሮ የሚገዛ ነው ፥ በዚህም ቃል ምትሐት የሚሉ እነ ማኒ ዋልጦስ ዝርው የሚሉ እለ መርቅያን ወልድ ፍጡር በመለኮቱ የሚል አርዮስ ተረተውበታል

፪ ወከማሁ ቀዳሚሁ እምቀዲሙ ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ።

፪ ያ ቃል በእግዚአብሔር አብ ህልው ነው እንዳልኩ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ህልው ነው ። እንድም ወዝንቱ ቀዳሚሁ እምቀዲሙ ይላል ይህ ቃል ከጥንት ጀምሮ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ህልው ነው በዚህም ቃል መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ የሚሉ እለ መቅዶንዮስ ተረተውበታል ቀዳሚሁ ቃል ባለው በቀዳሚ ኮነ ቃል ይላል ። እስመ ውእቱ ይቤ ወኮኑ ካለው ጋራ ንባብ ቢያሳብረው ምሥጢር አያሳብረውም እኒያን ተፈጠሩ ሲላቸው ነው ። እርሱን ግን በቅድምና ነበረ ሲለው ነውና ። በቀዳሚ ኮነ ቃል ባለው በቀዳሚ ሀሎ ቃል ይላል ፥ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ካለው ጋራ ንባብ ቢያሳብረው ምሥጢር አያሳብረውም እኒያን በቀዳማይ ዕለት በቀዳማይ ሰዓት ተፈጠሩ ሲላቸው ነው ። ጥንት አላቸው ጥንታቸው ዕለተ እሑድ ናት ፥ እርሱን ግን በቅድምና ነበረ ሲለው ነውና በቀዳሚ ሀሎ ቃል ፥ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ሀለወ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል ወከማሁ ቀዳሚሁ እምቀዲሙ ኀበ እግዚአብሔር ሀለወ ይላል ። እግዚአብሔር ብሎ ሦስትነታቸውን ተና

ገሪ አንበ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በአንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል አንድም ኀበ ኀበ ኀበ ብሎ ሦስትነታቸውን እግዚአብሔር እግዚአብሔር እግዚአብሔር ብሎ አንድነታቸውን ተናገረ ፡ ከዚህም አያይዘው ሊቃውንት ምሥጢረ ሥላሴን አምልተው አስፍተው አብዝተው ተናግረዋል ተርጕመዋል ። አምላክ ውእቱ አብ አምላክ ውእቱ ወልድ አምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ። ወኢይትበሀሉ ሠለስተ አማልክተ አላ አሐዱ እሙንቱ ምሥጢረ ሥላሴ ይትከፈል ወኢይትከፈል ፡ ይትከፈሉ በአካላት ወኢይትከፈሉ በመለኮት ሥላሴ በተዋሕዶ ወተዋሕዶ በሥላሴ ተጋብኦ በተከፍሎ ወተከፍሎ በተጋብኦ ኅቡራን እንበለ ተሌልዮ ወሊሉያን እንበለ ተድምርት እንዘ አሐዱ ሠለስቱ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ ይሤለሱ በአካላት ወይትወሐዱ በመለኮት ህልዋን እሙንቱ በአብ እንዘ ይሄልዉ በበአካላቲሆሙ ነአምን በአብ ከመ ህልው በወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወነአምን በወልድ ከመ ህልው በአብ ወመንፈስ ቅዱስ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ከመ ህልው በአብ ወወልድ እንዲል አንድም ምሥጢረ ሥላሴ ከጥንት ሲነገር ሲያያዝ የመጣ ነው እንጂ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ወኀ ፈሳሽ አይደለም በጥንተ ፍጥረት ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብለዋል ። ንግበር ፡ የሦስትነት ፡ አርአያነ ያንድነት ይህማ አንዱ አንዱን ንግበር ቢለው ይሆን የለምን ብሎ ከዚህ ይልቅ የጎላ ከዚህ ይልቅ የሚያስረዳ ንዑ ንረድ ወንከዕው ነገሮሙ ለዕጓለ እመ ሕያው እስመ አሐዱ ዘመድ እሙንቱ ብሏዋል ንዑ የሦስትነት ነገሮሙ ያንድነት ይህስ ቢሆን አንዱ አምላውኝ ለላውን ንዑ ቢላቸው ይሆን የለምን ብሎ ከዚህ ይልቅ የጎላ ከዚህ ይልቅ የሚያስረዳ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ አምላከ አበዊከ አምላከ አብርሃም አምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ ብለዋል ። አነ ያንድነት አምላከ አምላከ አምላክ የሦስትነት ፡ ዳዊትም ማህሉ ለእግዚአብሔር መልእ ምድረ ወበቃለ እግዚአብሔር ጸንዓ ሰማያት። ወእምእስትንፋሰ አፉሁ ኵሉ ኃይሎሙ ብሏል ። ፀልጁ ህልው ሁኖ ሥራ ሰሰ ሠራ።ዳግመኛም ዓቢይ እግዚአብሔር ወዓቢይ ኃይሉ ወአልቦ ትልቀ ስጥበቢሁ ። ዓቢይ እግዚአብሔር ። እግዚአብሔር አብ ወዓቢይ ኃይሉ እግዚአብሔር ወልድ ኃይሉ ስለ ተገለጸበት ። ወአልቦ ፡ ትልቀ ለጥበቢሁ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስለ ሀብቱ ብዛት ዳዊት ይህን በተናገረ በ፪፻ ዘመን ኢሳይያስ በዓመተ ሞተ ዖዝያን ንጉሥ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ነዋህ ወብሩህ ወምሉእ ቤተ ስብሐቲሁ ወሱራፌል ይቀውሙ ዓውዶ ለለ፩ በበ፮ ክነፊሆሙ በ፪ ከነፊሆሙ ይከድኑ ገጾሙ ወበ፪ቱ ክነፊሆሙ ይከድኑ እገሮሙ ወበ፪ቱ ክነፊሆሙ ይሠሩ እንጸረ ኅቡረ እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባኦት ፍጹም ምሉእ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ብሏል ። ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሦስትነት ምሉእ ያንድነት ። መልአኩም መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ብሏል ። ባለቤቱም ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብሏል ከዚህም እያያዘው ምሥጢረ ሥላሴን አምልተው አስፍተው አብዝተው ተናግረዋል አምላክ ውእቱ አብ ብለህ ህልው በወልድ እስኪል ጥቅስ እንዲህ በጥቂት ንባብ ብዙ ምሥጢር አናገረ ። እስመ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘከመዝ አምሳሊሁ ያመጽእ ብዙኃ ፍካሬ አኮ በብዙኅ ንባብ አላ በኅዳጥ እንዲል ።

፫ ወኵሉ ቦቱ ኮነ ።

፫ ሁሉ በርሱ ህልውና በርሱ አንድነት ተፈጠረ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ እምዘ ኮነ ከተፈጠረው ፍጥረት ግን ያለርሱ ህልውና ምንም ምን የተፈጠረ የለም ። በሐልዮ በአርምሞ የተፈጠረውን ለአብ የነቢብ የገቢሩን ለወልድ ሰጥተው የሚናገሩ አሉና በአርዮስም ያሳይቡታል ። ሸክላ ሠሪ መኖሪያዋን ሠርታ እንድትሠራ ፈጥሮ ፈጠረበት ካለ እርሱን በማን ፈጠረው ያሰኝበታልና ።

፬ ወዘሂ ኮነ በእንቲአሁ ቦቱ ሕይወት ውእቱ

፬ እርሱን ለማስመስገን እርሱን ለማስታወቅ በርሱ ሥልጣን የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ ሕይወት ነው ።

ወሕይወትሰ ብርሃኑ ለዕጓለ እመሕያው ውእቱ ። ሕይወትነቱም ለሰው ዕውቀት መሆን ነው ።

፭ ወብርሃንሰ ዘውስተ ጽልመት ያበርህ ወያርኢ

፭ በሥነ ፍጥረት ተመራምሮ የማያውቁት ዕውቀት በሰዋሬ ያለ ምሥጢርን ይገልጻል ። ለእመ ፈቀድከ ታእምር ዘንተ ብከ ሰማዕት ወካልዕ መምህር እምአፍአ ዘይመርሐከ ኀበ ዝንቱ ወኵሉ ዘተፈጥረ ለመፍቅደ ነባብያን ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ ወቦ ለተገብሮ እንዘ ኢየኃድግ ርእሶ ዘእንበለ ሰማዕት ። ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዓወቅ ለፍጥረቱ በፍጥረቱ እንዲል ። በሥነ ፍጥረት ተመራምረው ያመኑ ብዙ ናቸው ከዚያው ግን ከቀደሙ ሰዎች አብርሃም ከኋላ ሰዎች ሙሴ ጸሊም ።

ወጽልመትኒ ኢይረከቦ ።

በሥነ ፍጥረት የሚመራመርን ሰው ድንቁርና አያገኘውም ። ወኢይቀርቦ ።

ስንኳን ሊያገኘው አይደርስበትም ። አንድም ወዘሂ ኮነ በእንቲአሁ ብለህ መልስ ። እርሱን ለማስመስገን እርሱን ለማስታወቅ በርሱ ሥልጣን የተፈጠረፍጥረት

ሁሉ ሕይወት ነው ። ወሕይወትሰ ሕይወትነቱም በመመላለስ ። እፍራሲከኒ ሕይወት ውእቱ እንዲል ይህ አይወርድም ከዚህ ይቀራል ። እንድም ወዘሂ ኮነ እርሱን ለማመስገን እርሱን ለማስታወቅ በርሱ ሥልጣን የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ ሕይወት ነው ። ወሕይወትሰ ሕይወትነቱም ምግብ በመሆን እንድም ያበላልጣል ። ወሕይወትሰ ። ሕይወትስ ባለኝ አእምሮ ጠባይዕ ። ክብራስ ለጠባይዕ ነቢብ ወአእምሮ እንዲል ። ወብርሃንሰ ። በአእምሮ ጠባይዕ ተመራምሮ የሚያውቁት በሰዋሬ ያለ ምሥጢርን ይገልጣል ። እንዳባ ማቴዎስ በሥነ ፍጥረት ተመራምሮ በአእምሮ ጠባይዕ ዐውቆ ምግባረ ትሩፋት ሠርቶ በቅቶ ከመዓርገ ነጽሮ ደርሶ ከዚህ ሁኖ ሽቅብ ባየ ጊዜ እስከ ጽርሐ አርያም ቍልቍል ባየ ጊዜ እስከ በርባሮስ ያይ ነበር ወሶበ ሠረቀ ብርሃን አምላካዊ ውስተ ነፍስ ወተዋሐደት ነፍስ ምስሌሁ ያበውእ ለነፍስ ውስተ ኵሉን ጠባይዓት እለ ውስተ ሰማይ ወእለ ውስተ ምድር እንዲል ።

ወጽልመትኒ ኢይረክቦ በአእምሮ ጠባይዕ የሚመራመር ሰውን ድንቁርና አያገኘውም ስንኳን ሊያገኘው አይደርስበትም እንድም ወዘሂ ኮነ በእንቲአሁ ቦቱ ሕይወት ውእቱ ቦቱና በእንቲአሁ አንድ ወገን በርሱ ቃል የተነገረ ሃይማኖት ሕይወት ነው ። ወሕይወትሰ ሕይወትነቱም ለሰው ዕውቀት መሆን ነው ወብርሃንሰ በሃይማኖት ተመራምሮ ያወቁት ዕውቀት በሰዋሬ ያለ እግዚአብሔርን ይገልጻል ። አበዊነሂ ይሰምዩከ ቀባሬ ወዓውሎ በእንተ ሰዋሬከ እንዘ ደመናተ ብርሃን የዓውዱከ ወረሰየ ጽልመተ ምስዋሮ እስመ እሚን ትሬሰዮ ለሀኢሀለወ ከመ ዘሀለወ እንዲል ። ወጽልመትሰ ኢይረክቦ በሃይማኖት ያወቀን ሰው ክህደት አያገኘውም ወኢይቀርቦ ስንኳን ሊያገኘው አይደርስበትም እንድም በርሱ ቃል የተሰጠ ሥጋው ደሙ ሕይወት ነው ። ወሕይወትሰ ሕይወትነቱም ለሰው ዕውቀት መሆን ነው ። ወብርሃንሰ በሥጋው ደሙ ያወቁት ዕውቀት በሰዋሬ ያለ ምሥጢርን ይገልጣል ወሶበ ይበውእ ውስተ ልበ ንጹሕ ሶቤሃ ያነቅሆ ለተናግሮ እንዲል ከኃጢአት ነጽተው ቢቀበሉት ምሥጢር ይገልጣልና ወጽልመትኒ ሥጋውን ደሙን የተቀበለን ሰው ፤ ኃጢአት ኢይመውእ ወኢይሄይሎ ኃጢአት አይሠለጥንበትም ድል አይነሣውም ። እንድም ወቦቱ ኮነ ሕይወት ወቦቱ ሕይወት ውእቱ። ይላል በመጀመሪያው እንደ ሥነፍጥረት ባ፪ኛው እንደ ሃይማኖት ያስተረጕማል ። ዘወስተ ጽልመት ባለው በውስተ ጽልመት ይላል የላይ ቤት አብነት በጽልመተ ልብ በአይሁዳዊ አድሮ ምሥጢርን ይገልጣል ማለት ነው ።

፮ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘተፈነወ እምኀበ እግዚአብሔር ዘስሙ ዮሐንስ ።

፮ ስለ ሦስት ነገር ያመጣዋል ከወንድሞቹ ለማያያዝ ስሙን ለመናገር ምስክር ሦስት ለማድረግ ራሱ ዮሐንስ መጥምቅ እብ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበር ።

፯ ወውእቱ መጽአ ስምዐ ይኩን በእንተ ብርሃን ።

የብርሃንን ነገር ይመሰክር ዘንድ የመጣ ። እንድም ለስምዕ ይላል አብነት የብርሃንን ነገር ለመመስከር የመጣ ።

ከመ ኵሉ ይእመን እምኔሁ ሰው ሁሉ ከርሱ ተምሮ ያምን ዘንድ ። እንድም በዘእምኔሁ ከርሱ በተገኘ ትምህርት ያምን ዘንድ እንድም ቦቱ ሰው ሁሉ በርሱ ያምን ዘንድ ።

፰ ወለሊሁሰ ኢኮነ ብርሃነ ።
፰ እርሱ ብርሃን አይደለም ።
ዳዕሙ ስማዕተ ይኩን በእንተ ብርሃን ።
የብርሃንን ነገር ይመሰክር ዘንድ እንጂ ዝንቱ ማኀቶት ብሎ ያመጣው የለምን ቢሉ የዮሐንስ ብርሃንነት የጸጋ ነው ። የጌታ ግን የባሕርይ ነውና ። እንድም በዮሐንስ ብርሃን ሕጸጽ አለበት ። በጌታ ብርሃንነት ግን ሕጸጽ የለበትምና ።

፱ ወብርሃን ጽድቅሰ ዘያበርህ ለኵሉ ሰብእ ዘመጽአ ውስተ ዓለም ።

፱ ለሰው ሁሉ ዕውቀትን የሚገልጥ እውነተኛ ብርሃንስ ወደዚህ ዓለም የሚመጣው ነው እንድም ወለሊሁሰ ኢኮነ ብርሃነ እርሱ ግን ብርሃን አይደለም ዮሐንስ ስማዕቱ ከልሐ በእንቲአሁ ብሎ እስኪያመጣው ሌላ ነገር አገባበት ወብርሃነ ጽድቅኒ ለሰው ሁሉ ዕውቀትን የሚገልጥ እውነተኛ ብርሃንም ወደዚህ ዓለም መጣ ።
ወውስተ ዓለም ሀሎ ።

መጽአ ብሎ ነበርና እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኅ ፈሳሽ በዓለሙ የሌለ ሁኖ አይደለም በዓለም ምሉእ ነው ።

ወዓለምኒ ቦቱ ኮነ ።
ሀሎ ብሎ ነበርና ሰው ቤት ሠርቶ በዚያ ተወስኖ እንዲኖር አይደለም ከዓለም በአፍኣ ነው ማለት ምሉእ ነው ።

ወዓለምሰ ኢያእመሮ ።
ዓለም ግን አላወቀውም ። ላይኛው ዓለም ሌላ ይህ ዓለም ሌላ ነው ።
፲፩ ውስተ ዚአሁ መጽአ ንግበር ሰብአ በአርአያነ

፲፩ ብሎ ወደ ፈጠራቸው ወገኖች መጣ ባሕርይ ለማንግት ።
ወእሊአሁሰ ኢተወከፍዎ ።
እርሳቸው ግን አላመኑበትም ።

፲፪ ወለእለሰ ተወከፍዎ ወሀቦሙ ሥልጣነ ውሉደ እግዚአብሔር ይኩኑ ለእለ እምኑ በስሙ ።

፲፪ ባያምኑበትስ ምን ይጎዳል ቢያምኑበትስ ምን ይጠቀማል ትሉኝ እንደሆነ ላመኑበትስ በስሙ ያመኑ የእግዚአብሔር ልጆች ይባሉ ዘንድ ግእዛንን ሰጣቸው ። ግእዛንማ የሚሰጥ በተፈጥሮ አይደለ ምን ቢሉ ወደኃጢአት ወደጣዖት ሂደው አሳድፈውት ነበርና አደሰላቸው ሲል ነው ። ከጥቀርሻ የተሰቀለውን ጋሻ ጦር አውርደው ወልውለው ሰንግለው ሥራ እንዲሠሩበት ።

፲፫ እለ ኢኮኑ እምነ ዘሥጋ ወደም
፲፫ ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ያልተገኙ ።

ወኢ እምሥምረተ ብእሲ ወብእሲት ።
ሴትና ወንድ ተዋደው ከሚሠሩት ሥራ ያልተገኙ ። አላ እምእግዚአብሔር ተወልዱ በመንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ተወልደዋል እንጂ እንድም ውስተ ዚአሁ መጽአ ብለሀ መልስ ወልድየ ዘበኵርየ ወዳላቸው ወደእስራኤል መጣ ። ወሖረ እምቅድመ ባዕዳን ኀበ እለ እምደመ እስራኤል እንዲል ወእሊአሁሰ ወልድየ ዘበኵርየ ያላቸው እስራኤል ግን አልተቀበሉትም ማርያ አላመኑበትም ወለእለሰ ተወከፍዎ ቢያምኑበትስ ምን ይጠቀማል ባያምኑበትስ ምን ይጎዳል ትሉኝ እንደሆነ ላመኑበትስ ልጅነት ሰጣቸው ለእለሰ ተወከፍዎ ለእሩ እምኑ በስሙ እንድ ወገን እለ ኢኮኑ ። ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ያልተገኙ ወኢእምሥምረተ ብእሲ ወብእሲት ሴትና ወንድ ተዋደው ከሚሠሩት ሥራ ያልተገኙ በሃይማኖት ከእግዚአብሔር ተወልደዋል እንጂ ከዚህ ያልተገኘ ምን አለ ቢሉ ሥራውን ከተውት ብሎ እስመ ኀደግን አበ ቀዳማዌ ዘውእቱ አዳም ዘቦቱ ማሰነ እንዲል

፲፬ ወውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ማቴ ፡ ፩ ፲፮ ፡ ሉቃ፡ ፪፡ ፯ ።

፲፬ እምእግዚአብሔር ተወልዱ ብሎ ነበርና ግዙፉኑ ከረቂቁ እንደምን ይወለዳሉ ትሉኝ እንደ ሆነ ረቂቁም እንጂ ገዘፈ ረቂቁም ከገዘፈ ግዙፉኑም ከረቂቁ ይወለዳሉ ለማለቅ እንዴህ አለ እንድም መጽአ ብሎ ነበርና እንደ ወትሮ የረድኤት ያይደለ ያ ቃል የኵነት ሥጋ ሆነ ። እንድም ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ነበርና በቅድምና የነበረ ያ ቃል ሥጋ ሆነ ። ወኀደረ ላዕሌነ ።

በኛም አደረ ። የኵነት የተዋሕዶ ኅድረት ። ኮነ ያለውን ይዘው ተለወጠ እንዳይሉ ኅደረ አለባቸው ኅደረ ያለውን ይዘው ኅድረት እንዳይሉ ኮነ አለባቸው ። ኮነና ኅደረ እንደ አለቃና እንደጠባቃ ይጠባበቃሉ ። ላዕሌነ ማለቱ ግን ሥጋ በቅድምና ነበረ ባሕርዩን አግዝፎ ታየ ምትሐት ውላጤ የሚሉ መናፍቃን አሉና ላዕሌነ አለባቸው ።ላዕሌነ ባለው በውስቴትነ ይላል በጽርእ ምላሽ እንደ መስኖ ውሀ ገብቶ ወጣ እንጂ ነፍስን ኢልተዋሐደም የሚሉ መናፍቃን አሉና ላዕሌነ ባለው ሥጋን ። በውስቴትነ ባለው ነፍስን እንደ ተዋሐደ ሰማጠየቅ ላዕሌነ በውስቴትነ አሉ ። ወሰወሮ እምኔነ በዘእምኔነ ቃልን በኛ ባሕርይ ሰወረው በተሰውሮተ ቃለ እግዚአብሔር በዘመድነ እንዲል ። እንድም ሥጋን ከኛ ሰወረው በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ አደረገው እንድም ሥግው ቃልን በርቀቱ አጸናው ። እፎኑ ኢየእምኑ እሙራን ሰብአ ከመ እምድኅረ ተሠገወ ነበረ ከመ ቃለ እንዲል ።

ወርኢነ ሲብሐቲሁ ከመ ስብሐተ ፩ዱ ዋሕድ ለአቡሁ ላባቱ እንዳንድ ልጅ ከብር የሚሆን ክብሩን እየንለት ። ልጅ ላባቱ እንድ የሆነ እንደሆነ ደጃፍ የመሰሰው ማጄት የጐረሰው ገንዘቡ ነው ። እሱም እስመ ኵሉ ዘቦ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ እንዲል ያባቱ ገንዘብ ሁሉ ገንዘቡ ነውና ። እንድም ወይሰገድ ከመ ዋሕድ እንዲል ። እንዳንድ ልጅነቱ ክብሩን እየንለት። እንደም ስብሐቲሁ ለዋሕድ ከመ ስብሐተ አሐዱ አቡሁ ፡ ያባቱን ጌትነት በደብረ ሲና እንዳየነ የርሱንም ጌትነት በዮርዳኖስ በደብረ ታቦር እየነ ። እንድም አባቱ በኤልያስ አድሮ አንድ ምውት በኤልሳዕ አድሮ ሁለት ምውት ሲያሥነሣ እንዳየነ እርሱም ሰው ሁኖ ያራት ቀን ሬሳ እልዓዛርን የለት ሬሳ ወልደ መበለትን ወለተ ኢያዔሮስን ሲያሥነሣ እየንለት ። ለሐዲሱስ ይሁን ለብሉዩ ወዴት ነበርና ርኢነ አለ ቢሉ የነሙሴን ዓይን ዓይን አድርጐ አባ ሕርያቆስ እርሱ ሳይኖር የሐዋርያትን መብል መብል አድርጎ ንሕነ እሙንቱ እለ በላዕነ ምስሌሁ እንዳለ ።

ዘምሉእ ጸጋ ።
ጸጋን የተመላ ። ጸጋ አለው የባሕርይ ክብሩን ለኛ የሚሰጠው ስለሆነ ወዘመለኮቱ ጸጋ ምሉእ እንዲል ወጽድቀ ። ጽድቀ አሚንን

ወሞገሰ ።   ስርየተ ኃጢአትን ። እንድም ዘምሉእ ወፍጹም በጸጋ ወበጽድቅ ወበሞገስ ይላል አብነት ።

፲፭ ዮሐንስ ሰማዕቱ በእንቲአሁ ከልሐ ወይቤ
፲፭ ወለሊሁሰ ኢኮነ ብርሃነ ብሎ ሌላ ነገር አግብቶበት ነበርና ከነገሩ ተመለሰ ። እንድም ሌላም ማግባት አይደለም እንዴህ እንደሆነ እገሌ ታውቁልኝ ብሎ ምስክር እንደማብዛት ያለ ነው ምስክሩ ዮሐንስ የርሱን ነገር ጮሆ ተናገረ መጮሀስ የሰው ጮሆ የተናገሩት ከሩቅ እንዲሰማ የርሱም ነገሩ ጽንፍ

እስከ ጽንፍ ተሰምቷልና ።
ዝውእቱ ዘእቤለክሙ እነ በእንቲአሁ ይመጽእ እምድኅሬየ ብእሲ ዘሀሎ እምቅድሜየ ። ከኔ አስቀድሞ የነበረ ከኔ በኋላ ይመጣል ያልኋችሁ ሰው ይህ ነው ። ሀሎ እምቅድሜየ እንደአምላክነቱ ፤ ብእሲ ይመጽእ እምድኅሬየ እንደሰውነቱ ።

እስመ እምቅድሜየ ውእቱ ኮነ ከኔ በፊት ነበርና ማለት የባሕርይ አምላክ ነውና ።

፲፮ እስመ እምተረፈ ዚአሁ ነሣእነ ኵልነ ጸጋ በዲበ ጸጋ ። ፩. ጢሞ ፮ ፥ ፲፯ ።

፲፮ ከፍጹም ጌትነቱ ከተፈጸመለት ሀብቱ በዐሥርቱ ቃላት ላይ ወንጌልን ። በመንፈስ ረድኤት ላይ መንፈስ ልደትን ። በእእምሮ ጠባይዕ ላይ መንፈሳዊ እእምሮን ተቀበልን ። አንድም ነሣእነ ጸጋ ሀየንተ ጸጋ ይላል ። ነሣእነ ጸጋ ። ወንጌልን ባሠርቱ ቃላት ስለ ጸናኝ ፈንታ ። ነሣእነ ጸጋ ። መንፈስ ልደትን በመንፈስ ረድኤት ስለ ጸናን ፈንታ ነሣእነ ጸጋ እእምሮ መንፈሳዊን። በእእምሮ ጠባይዕ ስለ ጸናኝ ፈንታ ። አንድም ነሣእነ ጸጋ በዲበ ጸጋ ሀየንተ ጸጋ ይላል ፤ በዐሥርቱ ቃላት ላይ ወንጌልን ። ባሠርቱ ቃላት ስለጸናኝ ፈንታ ። ዮሐንስ መጥምቅ ወዴት ነበርና ነሣእነ አለ ቢሉ እንዳይቀርበት ያውቃልና ወእምተረፈ ዚአሁ ይላል ።
ርኢነ ላለው ዋዌ ።

፲፯ እስመ ኦሪት በሙሴ ተውህበት ለነ ።

፲፯ ኦሪት በሙሴ ተሠርታልናለችና ። በዲበ ጸጋ ላለው ።

ወጸጋሰ ወጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ኮነ ለነ ።
ጸጋ ጽድቅ ወንጌል ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ተሠርታልናለችና ። ነሣእነ ጸጋ አንድም ኦሪት በሙሴ ተሰርታልናለች እኮን ፤ ጸጋ ጽድቅ ወንጌል ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ተሠርታልናለች ።

፲፰ ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ። ፩ ጢሞ ፮ ፲፮ ፩ ፥ ዮሐ ፬ ፲፪ ።

፲፰ ርኢነ ብሎ ነበርና እግዚአብሔርን ማን ያየው አለ ትሉኝ እንደሆነ እውነት ነው እግዚአብሔርንስ ከቶ በባሕርዩ ያየው የለም ። እስመ በአንጽሖ መንፈስ ርእይዎ ነቢያት ለእግዚአብሔር ወተናጸሩ ገጸ በገጽ ይል የለምን ቢሉ ባሕር አየሁ እሳት አየሁ ሰማይ አየሁ ማለት ነው እንጂ በባሕርዩ ያየው የለም ። ኢላ ወልድ ዋሕድ ዘሀሎ ውስተ ሕፅነ አቡሁ ውእቱ ነገረ ባባቱ ዕሪና ያለ ወልድ በባሕርዩ አይቶ ነገረን እንጂ አንድም ከነቢያት ወገን ልጅ ሆኖ ያየው የለም ልጁ ልጅ ሆኖ በባሕርይ አይቶ ነገረን እንጂ ።

በእንተ ስምዑ ለዮሐንስ መጥምቅ ።

፲፱ ወዝንቱ ውእቱ ስምዑ ለዮሐንስ ።
፲፱ የዮሐንስ ወንጌላዊ ምስክርነቱ ይህ ነው ።

ርኢነ ስብሐቲሁ ያለው ኢመ ለአኩ ብለህ ለዮሐንስ መጥምቅ ስጥ ። አንድም የዮሐንስ መጥምቅ ምስክርነቱ ይህ ነው ይመጽእ እምድኅሬየ ዘሀሎ እምቅድሜየ ያለው ። ወኢመ ለአኩ ብለህ ያለፈውንም የሚመጣውንም ለዮሐንስ መጥምቅ ስጥ ። አንድም የዮሐንስ መጥምቅ ምስክርነቱ ይህ ነው ። ዝ ያለውን ያመጣዋል ።

ኢመ ለአኩ ኀቤሁ አይሁድ እምኢየሩሳሌም ካህናተ ወሌዋውያነ ።

አይሁድ ከኢየሩሳሌም ካህናት ሌዋውያንን በላኩ ጊዜ ሌዋውያን ካህናትማ ይልኩን ይላኩ ቢሉ ደግን ሰው ከደግ መላክ ልማድ ነው ። ታሪክ የሁለቱን ነገድ ተኩል በዮርዳኖስ ማዶ ግንብ መሥራት ጀመሩ ጣዖት ለማምለክ ግንብ ይሠሩ ጀመሩ ብለው ለኢያሱ ነገሩት ቦታ ጠቧችሁ እንደሆነ ወደኔ ኑ እንጂ ጣዖት አታምልኩ ብሎ ዐሥሩን የቤት አለቆች ፊንሐስን ሊቀ ካህናቱን ላከ ። ጣዖትስ እንዳናመልክ አምላክ እስራኤል ያውቃል ነገር ግን ከዘመን ብዛት የተነሣ ልጆቻችሁ ልጆቻችንን እናንተ ከዚህ ምን አላችሁ አባቶቻችሁ በዮርዳኖስ ዳር ቀርተው የለም እንዳይሏቸው በቤተ መቅደስ አንጻር ይሁንልን ብለን ነው እንጂ ብለውታል ። አንድም መልክተኞችን በቃል አምጣ ። አይሁድ ካህናት ሌዋውያን ወደርሱ በላኩ ጊዜ ።
ከመ ይሰአልዎ ወይቤልዎ መኑ አንተ ።
አንተ ማነህ ብለው ይጠይቁት ዘንድ ወኢመ ይቤልዎ ይላል ለአኩ ላለው ዋዌ በላኩበት እንዲህም ባሉት ጊዜ ።

፳ አምነ ወኢክህደ ከመ ኢኮነ ውእቱ ክርስቶስሃ ።

፳ አመነ እንጂ አልካደም ማለት ክርስቶስ ነህ ቢሉት አይደለሁም አለ እንጂ ነኝ አላለም ። በዝንቱ ስም ተሰምዩ ነቢያት ቅቡዓነ እንዲል ። ነኝ አይላቸውም ቢሉ ለልቡናቸው ምላሽ አይደለምና
፳፩ ወይቤልዎ መኑ አንተ
፳፩ አንተ ማነህ ።
ኤልያስኑ አንተ ።
ኤልያስን ነህ አሉት ።
ወይቤ ኢኮንኩ ። አይደለሁም አለ ።
እመሰ ትፈቅዱ ትትወከፍዎ ዝውእቱ ኤልያስ ዘሀለዎ ይምጻእ ፤ ይል የለምን ቢሉ ለልቡናቸው ምላሽ አይደለምና ወይቤልዎ ነቢዩኑ አንተ ።

ሙሴ ኢያሱ ነህ ።
ወይቤ አልቦ ።
አይደለሁም አለ ። ወወህበ ኃይለ ተነብዮ ለመጥምቅ እንዲል እኒያም ማስተማር ማጥመቅ ነው እርሱም ያስተምራቸዋል ያጠምቃቸዋል ነኝ አይላቸውም ቢሉ ለልቡናቸው ምላሽ አይደለምና ።

፳፪ ወይቤልዎ መኑመ አንተ እንከ ከመ ናይድእሙ ወናጠይቆሙ ለእለ ለአኩን ወፈነውነ

፳፪ ለአኩን በነገር ፈነውነ በእግር ለላኩን እንነግራቸው እናስረዳቸው ዘንድ እንኪያ ማነህ ።
መነ ትብል ርእሰከ ።
ማነኝ ትላለህ አሉት ።

፳፫ ወይቤ አንሰ ቃለ ዓዋዲ ዘይሰብከ በገዳም ወይብል ጺሑአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር በከመ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ።ኢሳ፥፵፥፫ማቴ፥፫፥፫ማር፥፩፥፫ሉቃ.፫፥፬

፳፫ እኔስ ኢሳይያስ እንደ ተናገረ የእግ‌ዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ ብዬ በገዳም የማስተምር ዐዋጅ ነጋሪ ነኝ ።

፳፬ ወእለሰ ተፈነዉ እምፈሪሳውያን እሙንቱ
፳፬ የተላኩት ግን ከፈሪሳውያን ነበሩ ።
፳፭ ወተስእልዎ ወይቤልዎ በእፎ አንከ ታጠምቅ ለእመ ኢኮንከ ክርስቶስሃ ።

፳፭ ቢሰጡን እንነዳ ቢነሱን እናረዳ የማይሉ ዶጋግ ናቸውና ። መላልሰው ይጠይቁታል ። ለምንት ሲል ነው ። በእፎ ትጼእል ሊቀ ካህናቲሁ እንዲል ። ክርስቶስን ካይደለህ ለምን ታጠምቃለህ ብለው ጠየቁት ክርስቶስ በመጣ ጊዜ እንዲያጠምቅ እነዘሐከሙ በማይ ንጹሕ ተብሎ ተነግሯል ወኢ ኤልያስሃ ። ኤልያስን ካይደለህ ለምን ታጠምቃለህ አለ የርዳኖስን ከፍሎ መሻገሩን ጥምቀት ብለውት ።
ወኢነቢየ ሙሴን ኢያሱን ካይደለህ ለምን ታጠምቃለህ ለኒያ እስመ ለኵሎሙ አበዊነ አጥመቆሙ ሙሴ በደመና ወበባሕር ወተጠምቃ እገሪሆሙ ስካህናት ተብሎ ተነግሮላቸዋል ።

፳፮ ወአውሥአ ዮሐንስ ወይቤሎሙ አንሰ አጠምቀክሙ በማይ ማቴዎስ ፫፥፲፩ ።

፳፮ እኔስ ለጠጅ ብርሌን ለልብስ ገላን እንዲያጥቡለት ለርሱ ጥምቀት በሚያበቃ ጥምቀት ለርሱ ተአምኖ ኃጣውእ በሚያበቃ ተአምኖ ኃጣውእ አጠምቃችኋለሁ አንድም በአፎ ብለህ መልስ ክርስቶስ ካይደለህ ለምን ሥርዓት ለዋውጠህ ታስተምራለህ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ሥርዓት ለዋውጦ እንዲያስተምር መቅደስ ትትሐነጽ እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ወእምዝ ትትመዘበር ተብሎ ተነግሮለታል ለኤልያስም ከመ ይሚጥ ልበ አበው ኅበ ውሉድ ተብሎ ። ለኢያሱም ፤ ነቢየ ያነሥእ ለክሙ እምአኃዊክሙ ተብሎ ተነግሮለታል ። ወአውሥአ ዮሐንስ ወይቤሎሙ አንሰ አጠምቀክሙ በማይ ምን ሥርዓት ለዋወጬ አስተማርኩ ። እኒያም በውኃ ያጠምቋችሁ ነበር ። እኔም በውኀ አጠምቃችኋለሁ ። ወማእከሌክሙ ሀሎ ይቀውም ዘኢተአምርዎአንትሙ ሥርዓት ለዋውጦ የሚያስተምር እናንተ የማታውቁት ከመካከላችሁ ቁሟል ፤ ኢተአምርዎ እንደ አምላክነቱ ይቀውም ። እንደ ሰውነቱ ።

፳፯ ዘይመጽእ እምድኅሬየ ውእቱ ዘሀሎ እምቅድሜየ ። ማር፥፩፥፯ ሉቃስ፥፫ ፲፯፥ ግብ ፲፫፥፲፭፥ ፲፮ ፲፱ ፬ ።

፳፯ ከኔ በኋላ የሚመጣው ከኔ አስቀድሞ የነበረው ነው አለ ፡ የባሕርይ አምላክ ነው ።
ዘኢይደልወኒ እፍታሕ ቶታነ አሣእኒሁ እምገሪሁ። ሃለግሩን ጫማ ልፈታ የማይገባኝ ። ዕጼር ማቴዎስ እደንን ማርቆስ ፡ እፍታሕ ሉቃስ ፥ መገናኛው ዮሐንስ እንዲህ ግን ስለሆነ እደንን ይቀድማል እፍታሕ ይከተላል ዕጼር መጨረሻ ነው ይህን ተካፍለው ጽፈዋል ።

፳፰ ወከመዝ ኮነ በቢታንያ በቤተ ራባ በማዕዶተ ዮርዳኖስ በኀበ ሀሎ ያጠምቅ ዮሐንስ ።

፳፰ ዮሐንስ ያጠምቅበት በነበረ በዮርዳኖስ ማዶ ቢታንያ ቤተራባ በሚባሉ አገሮች እንዲህ ያለ ጉባኤ እንዲህ ያለ ክርክር ተደረገ ። አንድም ቀድሞ አንያ ራባ የሚባሉ ነገሥታት ከተማ ሠርተውበት ኋላ ተፈትቷል ቀድሞ ከተማ ተሠርቶበት ነበር ኋላ ከተፈታ ዮሐንስ ያጠምቅበት በነበረ በዮርዳኖስ ማዶ እንዲህ ያለ ጉባኤ እንዲህ ያለ ክርክር ተደረገ ።

፳፱ ወእመ ሳኒታ ርእየ ዮሐንስ ለእግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይመጽእ ኀቤሁ ።
ወከመዝ ኮነ በቢታንያ በቤተራባ በማዕዶተ ዮርዳኖስ በኀበ ሀሎ ዮሐንስ ያጠምቅ ብሎ ነበርና ለዚያ ሳኒታ አለ ።
አንድም ሕዝቡ ሊጠመቁ በዋዜማው ተሰብስበዋልና ለዚያ ሳኒታ አለ ። አንድም ጌታ ባሥረኛው ሰዓት ሌሊት ተጠምቆ ሁለቱን ተቦታው ሂዶ አንግቷል ቢነጋ ለመሰናበት መጥቷል ላሥሩ ስዓት ሁለቱን ሳኒታ አለው ።

፳፱ በነጋው ዮሐንስ ጌታ ወደርሱ ሲመጣ ባየ ጊዜ ።
ወይቤ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያእትት ወያሴስል ኃጢአተ ዓለም ።
የሰውን ኃጢአት የሚያስተሰርይ የእግዚአብሔር መሥዋዕቱ እነሆ አለ ። እንዲህም ባለጊዜ የሕዝቡን ቢሉ መሥዋዕታቸውን የካህናቱን ቢሉ

ሕጋቸውን እንዳሳለፈባቸው ያጠይቃል ። ያአትት ወያሴስል ማለቱ ግን ስለ ጊዜው ስለዘላለሙ ስለ ሥጋ ስለ ነፍስ ስለ ሕዝብ ስለ አሕዛብ ለማለት የአትት ባለው ዘይጸውር የሚል አብነት ይገኛል ቀድሞ የብሉይ ሊቀ ካህናት እጁን ከበጉ ራስ አድርጎ ይጸልይ ነበር ኃጢአታችን ባንተ ምክንያት ይሰረያል ሲል በዚያ ግሥ እንዲህ አለ ።

፴ ዝንቱ ውእቱ ዘእቤለክሙ አነ በእንቲአሁ ይመጽእ እምድኅሬየ ብእሲ ዘሀሎ እምቅድሜየ ።

፴ ከኔ አስቀድሞ የነበረው ከኔ በኋላ ይመጣል ያልኳችሁ ሰው ይህ ነው ።

እስመ እምቅድሜየ ውእቱ ኮነ

ከኔ አስቀድሞ ነበርና ማለት የባሕርይ አምላክ ነውና ።

፴፩ ወአንሰ ኢየአምሮ ።

፴፩ እኔ ግን አላውቀውም ። ቃል ለቃል ተጨዋውቶ ማማለጃ በልቶ ተዘምዶተ ሥጋ ኑሮት አድልቶ ይሉኛል ብሎ ። አንድም የዮሐንስ አስተዳደግ በገዳም ። የጌታ አስተዳደግ በዓለም ነውና ። አንድም ካንድ ቀን በቀር አይቶት ባያውቅ ። ታሪክ ከግብጽ ከወጡ በኋላ ጌታ ወደ ደብረ ሲና እያቀና ሲያይ አይታ እመቤታችን ልጄ ወደዚያ ምን ታያለህ አለችው ። ኤልሳቤጥ እኅትኪ አዕረፈት አላት ፤ ደመና አድርሷቸዋል ስምዖንና ዘካርያስ በአካለ ነፍስ መጥተው ቀብረዋት ሄደዋል ። እመቤታችን እንዲህ ከሆነ ይዘነው እንሂድ አለችው ። ሰማያዊ አባቱ ያዘዘለት ቦታው ይህ ነው አይሆንም አላት ያን ጊዜ ዐሥራ አንድ ዓመት ሁኖት ነበር ቢሉ ዓሥራ ዘጠኝ ዓመት ኑሮ ይገናኛሉ።ያን ጊዜ ዘጠኝ ዓመት ሁኖች ነበር ያሉ እንደሆነ ሃያ አንድ ዓመት ኑረው ይገናኛሉ። ያላንድ ቀን አይቶት ባያውቅ። አንድም እኔ የማላውቀው ሁኖ አይደለም ፤

ዳዕሙ ከመ ያእምርዎ እሥራኤል በእንተዝ መጻእኩ አነ ከመ አጥምቅ በማይ ።

እስራኤል ያውቁት ዘንድ ስለዚህ በውኃ ላጠምቅ መጣሁ ማለት ላስተምር ታዝዤአለሁ እንጂ ።

፴፪ ወነገረ ስምዖ ዮሐንስ ። ማቴ፡፫፡፲፮ ማር፡ ፩፡፲ ሉቃ ፫ ፡ ፳፪ ።

፴፪ አብ ለወልድ የመሰከረውን ። አንድም ለወልድ የተመሰከረውን ። አንድም ዮሐንስ ምስክርነቱን ተናገረ ።

ወይቤ ርኢኩ መንፈስ ቅዱስ እንዘ ይወርድ እምሰማይ ከመ እንተ ርግብ ወይነብር ዲቤሁ ርኢኩን ቢያዩ መንፈሰ ቅዱስ ይወርድን ቢያዩ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ ሲቀመጥበት አየሁ ብሎ መሰከረ ።

፴፫ ወአንሰ ኢየአምሮ ።

፴፫ እኔ ግን አላውቀውም ።

ወባሕቱ ዘፈነወኒ ከመ አጥምቅ በማይ ውእቱ ይቤለኒ ዲበ ዘርኢከ ይወርድ መንፈስ ቅዱስ ወይነብር ዲቤሁ ውእቱኬ ዘያጠምቅ በመንፈስ ቅዱስ ።

ማየት በፊት መንገር ወደ ኋላ ነው ብሎ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥበት ባየኸው ማየት ላይ ። አንድም ዲቤሁ ዘርኢከ ። ያየኸው እርሱ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ እንጂ ። አንድም መንገር በፊት ማየት ወደኋላ ነው ብሎ ። ዲበ ዘትሬኢ ፤ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ሲቀመጥበት በምታየው ማየት ላይ ። አንድም ዲቤሁ ዘትሬኢ የምታየው እርሱ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ እንጂ ።

፴፬ ወሰልየ ርኢኩ ወአነ ሰማዕቱ ።

፴፬ እኔ አየሁ መሰከርኩ ።

ከመ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለእግዚአብሔር ።

ይህ የእዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ።

በእንተ ቀዳማውያን አርድእተ ኢየሱስ ።

፴፭ ወበሳኒታ ካዕበ እንዘ ይቀውም ዮሐንስ ወክሌኤቱ እምአርዳኢሁ ።

፴፭ ተራ ሳኒታ ። አንድም የሳኒታ ሳኒታ ። አንድም የሄደባትን ለተመለሰበት ሳኒታ አለው፡ በነጋውም ዮሐንስ ከሁለቱ ደቀ መዛሙርት ጋራ ቁሞ ሳለ ። ሐተታ ዮሐንስና እንድርያስ ናቸው ።

፴፮ ርእዮ ለኢየሱስ እንዘ የሐውር ።

፴፮ ጌታን ሲሄድ አይቶት ።

ወይቤ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያአትት ወያሴስል ኃጢአተ ዓለም ።

የእግዚአብሔር በግዑ ማለት የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሰርይ የእግዚአብሔር መሥዋዕቱ እነሆ አላቸው ።

፴፯ ወሰምዕዎ ክልኤሆሙ አርዳኢሁ እንዘ ይብል ከመዝ ።

፴፯ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱም እንዲህ ሲል ሰምተው ።

ወተለውዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ከዳረገኸንማ ብለው ጌታን ኢየሱስን ተከተሉት ።

፴፰ ወተመይጦ እግዚእ ኢየሱስ ርእዮሙ እንዘ ይተልውዎ ፪ሆሙ አርዳኢሁ ለዮሐንስ ።

፴፰ ጌታም ሁለቱ የዮሐንስ ተማሪዎች ሲከተሉት ተመልሶ አያቸው ።

ወይቤሎሙ ምንተ ተኀሥሡ ምን ትሻላችሁ አላ

ቸው ሰው ሲከተል ዝም ማለት አይገባምና ።
ወይቤልዎ ረቢ ዘበትርጓሜሁ ሊቅ ብሂል ፡
ትርጓሜው መምህር ሆይ ማለት ነው ።
አይቴ ተኃድር ።
ወዴት ታድራለህ አሉት ። ደግን ሰው ከመንገድ ኢቁሞ ማነጋገር ፈሊጥ አይደለምና ።

፴፱ ወይቤሎሙ ንዑ ትርአዩ ኀበ እኀድር።
፴፱ ታዩ ዘንድ ኑ አላቸው ። ወይቤሎሙ ንዑ ትርአዩ ፡ መጥታችሁ እዩ አላቸው ።
ወሖሩ ወርእዩ ኀበ የኃድር ።
ሂደውም የሚያድርበትን እዩ ወወዓሉ ኀቤሁ ይእተ ዕለተ እስከ ዓሥሩ ሰዓት ።
በዚያን ቀን እስከ ዐሥር ሰዓት ከእርሱ ዘንድ ዋሉ አለ ሲማሩ ። ምነው በሚያመጣው አኮኑ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ሰዓቱ ለዕለት ይል የለምን ቢሉ አንዱ የሄዱበት አንዱ የተመለሱበት ነው ። አንድም ሁለት ሰዓት ሳይልፈው ሄደው ሲመሽ ተመልሰዋል ። እንድም ማለዳ ሄደው ሁለት ሰዓት ሲቀር ተመልሰዋል ። አንድም አይቴ ተኃድር ብለህ መልስ ፡ እንደምን ባለ ሰውነት ታድራለህ አሉት ንዑ ትርአዩ እስራኤል ዘነፍስ ትባሉ ዘንድ እመኑ አላቸው ወሖሩ ወርእዩ፡እስራኤል ዘነፍስ ተባሉ ወወአሉ ኀቤሁ እስከ ዓሥሩ ሰዓት ። እስከ ዐሥሩ ማዕርጋት ደረሱ

፵ ወአሐዱ ውእቱ እንድርያስ እኁሁ ለስምዖን ጴጥሮስ እምክልኤቱ እለ ሰምዑ በኀበ ዮሐንስ ወተለውዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፵ ዮሐንስ ነዋ በግዑ ሲል ሰምተው ጌታን ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥርስ ወንድም እንድርያስ ነው ፡ የርሱን ሳይናገር ቀረ ስለ ትሕትና ። ይህስ እንዳይሆን የርሱንም ረድዕ ዘያፈቅሮ ብሎ በኋላ ያመጣዋል ብሎ እርሱ ከዚህ ነገር የለውም ። እንድርያስን ግን ጴጥሮስን ሳበ የሚለው ነውና ።

፵፩ ወለሊሁ አቅደመ ረኪበ እኁዋሁ ለስምዖንሃ ።

፵፩ እርሱ አስቀድሞ ወንድሙን ስምዖንን አገኘ ።
ወይቤሎ ረከብናሁ ለመሲሕ ዘይብልዎ ክርስቶስ። ክርስቶስ የተባለ መሲሕን አገኘነው ። ማስያስ በዕብራይስጥ ክርስቶስ በጽርእ ። መሲሕ በዓረብ ቅቡዕ በግእዝ ።

፵፪ ወውእቱ ወሰዶ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ።
፵፪ እርሱም ወደጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይዞት ሄደ ።
ወሶበ ርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ለስምዖን ይቤሎ አንተኑ ስምዖን ወልደ ዮና ።
ጌታም ባየው ጊዜ የዮና ልጅ ስምዖን አንተ ነህ አለው ። አባቴን ካወቀ አክብሮ ያኖረኛል ብሎ እንዲከተለው ። አንድም ወልደ ዮሐንስ ዘዮና ይላል። የዮሐንስ ልጅ የዮና ልጅ ስምዖን አንተ ነህ አለው ። አንተሰኬ ትሰመይ ኬፋ የሚለው ነውና አባቴን እያቴን ማወቁ የባሕርይ አምላክ እንጂ ቢሆን ነው ብሎ ነገሩን እንዲቀበለው ።
አንተኬ ትሰመይ ኬፋ ።
አንተስ መሠረት ትባላለህ ዘበትርጓሜሁ ጴጥሮስ በትርጓሜው ጴጥሮስ ማለት ነው ። ኬፋ በዕብራይስጥ ጴጥሮስ በጽርእ ። ኰኵሕ በዓረብ ። በግእዝ እብን ኰኵሕና እብንስ አንድ ወገን ነው ብሎ በዓረብ እልሐጅር ይላል ።

፵፫ ወበሳኒታ ፈቀደ ይሑር ገሊላ ።
፵፫ የሳኒታ ሳኒታ ተራ ሳኒታ ። አንድም አርድእተ ዮሐንስ ለመጡበት ሳኒታ አለ ። በነጋውም ወደ ገሊላ ሊሄድ ወደደ ።
ወረከቦ እግዚእ ኢየሱስ ለፊልጶስ ።
ጌታ ፊልጶስን አገኘው ።
ወይቤሎ ትልወኒ ።
ተከተለኝ አለው ። ለጊዜው በእግር ፍጻሜው በግብር ምሰለኝ አለው ።

፵፬ ወውእቱ ፊልጶስ ዘቤተ ሳይዳ ዘገሊላ እምሀገረ እንድርያስ ወጴጥሮስ ።

፵፬ ይህ ፊልጶስም የእንድርያስና የጴጥሮስ አገር የምትሆን የቤተ ሳይዳ ሰው ነው ። እኒያ ሲያምኑ አይቶ አመነ ለማስት ።

፵፭ ወረከቦ ፊልጶስ ለናትናኤል ዘፍ፡፵፱፡ ፲ ዘዳ፡ ፲፰፡፲፰ ኢሳ፡ ፵፡፲ ። ኤር ፳፫፡፭ ሕዝ፡ ፴፬፡፳፫ ዳን፡፱፡፳፬

፵፭ ፊልጶስም ናትናኤልን አገኘው መሳሳብ ሆነ ።
ወይቤሎ ረከብናሁ ለኢየሱስ ወልደ ዮሴፍ እምና ዝሬት ዘጸሐፈ ሙሴ ውስተ ኦሪት ወነቢያት ተነበዩ በእንቲአሁ ። ሙሴ በኦሪት የጻፈለትን ። ነቢያትም ትንቢት የተናገሩለትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አገኘነው አለ ። ያላዋቂ ወታደር አነጋገር አንድም ዐውቃለ ብሎ አይሁድ የዮሴፍ ልጅ የሚሉትን የናዝሬቱን ኢየሱስን ሙሴ በኦሪት የጻፈለት ነቢያትም ትንቢት የተናገሩለት ሁኖ አገኘነው ።

፵፮ ወይቤሎ ናትናኤል ቦኑ ይትከሃል እምና ዝሬት ከመ ይፃ እኄር ብእሲ ።

፵፮ ናትናኤልም በውኑ ከናዝሬት ደግ ሰው ይገኝ ዘንድ ይቻላልን አለው ፡ እንደ ጭልጋ የወንበዴ የቀጥቃጭ አገር ናትና ። ዘቦቱ ሠናይት ይላል ። ሀብትኬ ሠናይ መንፈስ ቅዱስ እንዲል ። ልጅነትን ለራሱ ገንዘብ አድርጎ ለሌላው የሚያድል ደግ ሰው ይገኝ ዘንድ ይቻላልን

ወይቤሎ ፊልጶስ ነዓ ትርአይ ፡
ተከራክሮ ማስረዳት ባይቻለው መሆኑንም አለመሆኑንም መጥተህ እይና ተረዳ አለው ።

፵፯ ወሶበ ርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ለናትናኤል እንዘ ይመጽእ ኀቤሁ ።

፵፯ ኢየሱስም ናትናኤልን ወደርሱ ሲመጣ አየው ።
ወይቤ በእንቲአሁ ነዋ ዘበአማን እስራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሑት ውስተ ልቡ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወደርሱ ሲመጣ ናትናኤልን ባየው ጊዜ በውነት ክዳት ተንኮል የሌለበት እስራኤላዊ እነሆ ብሎ ስለርሱ ተናገረ ። እስራኤል ማለት ሕሊና ዘይሬእዮ ለእግዚአብሔር ፡ ነጸሪ ከሃሊ ምስለ አምላኩ ፡ ሕዝበ እግዚአብሔር ማለት ነው ።
ወይቤሎ ናትናኤል በአይቴ ተአምረኒ ።
ናትናኤልም ወዴት ታውቀኛለህ አለው ።

፵፰ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ እምቅድመ ይጸውዕከ ፊልጶስ ርኢኩከ በታሕተ ዕፀ በለስ

፵፰ ጌታም ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ አለው በቅትለተ ሕፃናት ጊዜ እናቱ በቀፎ አድርጋ ከበለስ ሥር ሰውራው ነበርና ። ያን ጊዜ ያዳንኩህ እኔ ነኝ ሲል ፡ አንድም ሰው ገድሎ አስቀብሮ ነበርና የጎልማሳ ሚስት ቀምቶ የማይገባ ሥራ ሲሠራ ነበርና ዐውቅብሃለሁ ሲለው ነው። አንድም ባለጸጋ ነው ከዚያ ሁኖ ወይፋፍን ሲያስፈትን ፈረስ በቅሎ ሲያስገራ ይውል ነበርና ። አንድም ምሁረ ኦሪት ነው ከዚያ ሁኖ የተነገረው ትንቢት ደረሰ የተቈጠረው ሱባኤ ቀረ እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ይውል ነበርና ዐውቅልሃለሁ ሲለው ነው አንድም የበለስ ቅጠሉ ሰፊ እንደሆነ ኃጢአት ሰፍናብህ አየሁህ ሲለው ነው ።

፵፱ ወአውሥአ ናትናኤል ።
፵፱ ናትናኤልም መለሰ ።

ወይቤሎ ረቢ አማን አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ። መምህር ሆይ በውነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ።
ወንጉሠ እስራኤል አንተ ።
የእስራኤልም ንጉሣቸው አንተ ነህ አለው ።
፶ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ
፶ ጌታም መለሰ ።

ወይቤሎ እስመ እቤለከሁ ርኢኩከ በታሕተ ዕፀ በለስ ተአምን ከዕፀ በለስ ሥር አየሁህ ብልህ አመንከ ። አንድም ሶበ እቤለከሁ ። ከበለስ ሥር አየሁህ ብየ ብልህ አመንከ ።

እምይእዜሰ ዘየዓቢ እምዝ ትሬኢ ።
ከእንግዴህስ ወዲህ ከዚያ የበለጠ ታያለህ አለው ። ሦስት ዓመት ከሦስት ወር የሚደረገውን ተአምራት ። አንድም ዕውቀቱ ከሌዋውያን ካህናት ጌትነቱ ከምድራውያን ነገሥታት እንዲበልጥ ለማጠየቅ፡ ትሬእዩ እንዘ ይትረኃዋ ሰማያት የሚል ነውና

፶፩ ወይቤሎ አማን እብለከሙ እምይእዜሰ ትሬእዩ እንዘ ይትረኃዋ ሰማያት ።

፶፩ ሰማያት ሲከፈቱ ።
ወመላእክቲ እግዚአብሔር እንዘ የዓርጉ ወይወርዱ ኀበ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
የእግዚአብሔር መልክተኞችም ወደ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ሲወጡ ሲወርዱ ታያላችሁ ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ። በሰማይስ መከፈት መዘጋት የለበትም ደጅ በተከፈተ ጊዜ የውስጡ እንዲታይ ያልተገለጠ ምሥጢር ሲገለጥ ተርኅወ ይላል እንጂ እርሱ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ መላእክት ሰው የጸለየውን ጸሎት የሠዋውን መሥዋዕት ለማሳረግ አይወጡም አይወርዱም ነበር ። እርሱ ሰው ከሆነ ወዲህ ግን የሚወጡ የሚወርዱ ሁነዋልና ። አንድም አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ እያሉ ርደቱን ዕርገቱን ለመንገር ።

ዘከመ ተገብረ ከብካብ በቃና ዘገሊላ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወአመ ሣልስት ዕለት ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ ።

፩ ወእመ ሳኒታ እንዘ ይቀውም ዮሐንስ ያለው እሑድ ። ወበሳኒታ ፈቀደ ይሑር ገሊላ ሰኞ ወአመ ሣልስት ማክሰኞ ። አንድም ከታች ውረድ ወአመ ሳኒታ ርእዮ ዮሐንስ ፡ እሑድ ጌታ ማክሰኞ ተጠምቆ ዕለቱን ሂዶ አርባው ቅዳሜ ይፈጸማል ። እሑድ ገብቶ ያድራል አርባውን ቀን እንዳንድ ቀን አድርጎ እሑድን ሳርባው ቀን ሳኒታ አለው ። በማቴዎስ ሃያ ኦምስቱን ዘመን እንዳንድ አድርጎ ወበውእቱ መዋዕል እንዳለ ። ወእመ ሳኒታ እንዘ ይቀውም ሰኞ ወአመ ሳኒታ ፈቀደ ያለውና ወአመ ሣልስት ፡ ማክሰኞ ሣልስትነቱ ለእሑድ ሳኒታነቱ ለሰኞ ፡ የገሊላ ክፍል በምትሆን በቃና በሦስተኛው ቀን ምሳ ሰርግ ተደረገ ።
ወሀለወት ሀየ እሙ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
እመቤታችን ከሰርግ ቤት ነበረች ። ቤተ ዘመድናትና ። አንድም ደግ ናትና ተጠርታ ።

፪ ወጸውዕዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
፪ ጌታን ጠሩት እናት ጠርቶ ልጅን መተው ሥርዓት አይደለምና ።

ወለአርዳኢሁኒ ውስተ ከብካብ ጸውዕዎሙ ያለበት ነው ደቀ መዛሙርቱንም ሰርግ ጠሯቸው መም ህር ጠርቶ ደቀ መዛሙርቱን መተው ሥርዓት አይደለምና ።

፫ ወሶበ ኀልቀ ወይኖሙ ትቤሎ እሙ ለእግዚእ ኢየሱስ ወይንኬ አልቦሙ ።
፫ ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ እመቤታችን ጠጅ አልቆባቸዋል ኣኮን አለችው እርሱ የማያውቀው ሁኖ አይደለም ፡ ዙሎ ዘይቤለከሙ ግበሩ ለማለት ነው እንጂ ።

፬ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ምንት ብየ ምስ ሌኪ ኦ ብእሲቶ ።

፬ ካንች ጋራ ምን አለኝ ማለት ወኀውን ጠጅ አድርግላቸው ብትዪኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ካንች ጋራ ምን ጸብ አለኝ አንድም ውኀውን ጠጅ አድርግላቸው ብትዪኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ውኀውን ጠጅ ላላደርግላቸው ከሰርግ ቤት ተጠርቼ መጥቻለሁን ውኀውን ጠጅ ላላደርግላቸው ነውን አላት ። አንድም በአምላክነቱ አገብሮ ተአዝዞ እንደሌለበት ለማጠየቅ ። አንድም ወኀወን ጠጅ አድርጌ የማጠጣቸው በኔ ፈቃድ ነው እንጂ ባንቺ ትእዛዝ ነውን አላት ።
ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜየ ፡
ነገር ግን ጊዜዬ አልደረሰም ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንዲል ። ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ አለውና በቀትር የሚሠራውን በሠለስት አይሠራውምና በሠለስት የሚሠራውን በነግህ አይሠራውምና ። አንድም ጠጁ ፈጽሞ አላለቀም ነበር ያለውንም አበርክቶት ቢሆን ያን አበረከተው ተብሎ ተአምራቱ ድንቅ ባልተባለም ነበርና ። አንድም ይሁዳ ወጥቶ ነበርና ከተአምራቱ እንጂ ቢለየኝ ከሞቱ ገባሁበት እንዳይል ።

፭ ወትቤሎሙ እሙ ለእግዚእ ኢየሱስ ለእለ ይትለአኩ ኵሎ ዘይቤለከሙ ግበሩ ።

፭ እመቤታችን የሚሠሩትን ያዘዛችሁን ሁሉ ሥሩ አለቻቸው ።

፮ ወሀለዋ ሀየ መሳብከት ስድስቱ እለ አብን በዘያጥኅሩ ቦቶን አይሁድ ንቡራት ሀየ ።

፮ ሀለዋና ንቡራት አንድ ወገን ። አይሁድ በሚያጠምቁባቸው ገንዘብ ያጠምቁባቸው ዘንድ የሚያጠምቁባቸው ስድስት የደንጊያ ጋኖች ከዚያ ነበሩ እንደምን አድርገው ይሠሩታል ቢሉ ያነጥጡታል ፡ ይህስ ሲነሣ ጭቃ እየሆን ያውካል ብሎ አብነ አልማስ የሚባል አለ ። ደንጊያውን ሁሉ እየሰበሰቡ ያቀረቡለት እንደ ሆነ ያቀልጠዋል እያስማሙ ይሠሩታል ።
ወያገምራ ለለ፩ በበ፪ቱ ወበበ፫ቱ መሥፈርት ዘቀሡት ሁለት ሁለት ሦስት ሦስት ማድጋ ይይዛሉ ሦስቱ ሁለት ሁለት ሦስቱ ሦስት ሦስት ዓሥራ አምስት ይሆናል ።
አንድም ስድስቱ በታናናሽ ሦስት ሦስት ይይዛሉ ዐሥራስምንት ይሆናል ። አንድም ስድስቱ በታላላቅ ሁለት ሁለትይይዛሉ። ዐሥራ ሁለት ይሆናል ።

፯ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለእለ ይትለአኩ ምልእዎንኬ ለእላ መሳብከት ማየ ።

፯ ጌታችን ኢየሱስ እኒህን ጋኖች ውኀ ሙሏቸው አለ ።
ጠመልእዎን እስከ ላዕሉን ።
እስከ ጉረሮዋቸው ።
ወእስከ አፉሆን ።
እስከ ከንፈራቸውም መሏቸው ። አንድም እስከ አፉሆን እስከ ከንፈራቸው ። ወእስከ ላእሉን ፣ እንደ ማር እንደ ቅቤ ቆለል እስኪል ።

፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ቅድኁዎንኬ ይእዜ ወስዱ ወሀብዎ ለሊቀ ምርፋቅ ።

፰ ቀድታችሁ ወስዳችሁ ላሳዳሪው ስጡት አላቸው ። ተአምራትስ ያደርጋል ነገር ግን አስተዳደር አያውቅም እንዳይሉት ። አንድም ሁሉ ጠጥቶ ስከሯል ጣዕም አያውቅም እርሱ ግን አልጠጣምና ጣዕም ያውቃል ብሎ ወወስዱ ወወሀብዎ ።
ቀድተው ወስደው ስጡት ።

፱ ወጥዒሞ አንከረ ሊቀ ምርፋቅ ውእቱ ማየ ዘኮነ ወይነ ።

፱ የምርፋቁ አለቃ ጠጅ የሆነውን ውኀ ቀምሶ አደነቀ ።

ወኢያአመረ እምኀበ አምጽእዎ ።
ካመጡበት ግን አላወቀም ።
ወገዛዕትስ እለ ቀድኀዎ የአምሩ ውእተ ማየ ዘኮነ ወይነ ሠራተኞች ግን ጠጅ የሆነውን ውኀ ያውቃሉ እስመ እሙንቱ መልዑ ማየ ምሉ ብሏቸው መልተዋልና ወጸውዖ ሊቀ ምርፋቅ ለመርዓዊ ።
የምርፋቁ አለቃ ሙሽራውን ዶኪማስ ብሎ ጠራው።

፲ ወይቤሎ ኵሉ ሰብእ ዘይሤኒ ወይነ ያቀድም አስትዮ ።

፲ ሰው ሁሉ ሸሎውን በርዳዳውን አስቀድሞ ያጠጣል ።
ወእምድኅረ ሰከሩ ያስቲ ዘይቴሐት ።
ከጠገቡ በኋላ ግን ተራውን ያጠጣል ። ቢጠጡ

ይጠጡት ባይጠጡ ቀምሰው ለብላቴኖቻቸው ይስጡዋቸው ብሎ ።

ወአንተሰ ዘይሴኒ ወይነ ዓቀብከ እስከ ይእዜ ።
አንተ ግን ሸሎውን በርዳዳውን እስካሁን አቆየህ ። አንድም ዓቀብከ ወአስተደኃርከ ይላል ፈጽመህ አቆየህ ።

፲፩ ወዝንቱ ውእቱ ቀዳሜ ተአምር ዘገብረ እግዚእ ኢየሱስ በቃና ዘገሊላ ።

፲፩ የገሊላ ክፍል በምትሆን በቃና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው የተአምራቱ መጀመሪያ ይህ ነው ። ሦስት ዓመት ከሚያደርገው አንድም ደገኛ ተአምራቱ ይህ ነው ቀዳሚሆሙ ለአሕዛብ አማሌቅ ቀዳሜ ተግባሩ ለእግዚአብሔር ብሂሎት እንዲል ። ሙሴ ውኀውን በሐልዮ ደም እንዳደረገው ። በሐልዮ ነውና ውሀውን ጠጅ ያደረገው ። ሙሴኒ ሚጠ ለማይ እምከዊነ ማይ ኀበ ከዊነ ደም እንዘ ኢይትናገር በአፉሁ ዳዕሙ በሕሊናሁ እንዲል።
ወእርአየ ስብሐቲሁ ። ተአምራቱን
አሳየ ። አንድም ጌትነቱን ገለጠ ።
ወአምኑ ቦቱ አርዳኢሁ ።
ደቀ መዛሙርቱ አመኑበት ። ሊጸፍ ባይቻል ነው እንጂ ጠይቀውታል ጠይቀዋቸዋል እርሱን ። ጠየቁት አላውቅም አለ እርሳቸውን ጠየቋቸው ውኀምሉ አለን መላን ቀድታችሁ ስጡ አለን ቀድተን ሰጠን ኋኛ ምን እናውቃለን ብለዋል ። አንድም ወአመ ሣልስት ዕለት ብለህ መልስ ። በሦስተኛው ክፍለ ዘመን ሥጋዌ ተደረገ ወሀለወት እሙ ጥበቡ ከሥጋዌ አስቀድሞ ነበረች ወጸውዕዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ወለአርዳኢሁ ነቢያት ጌታችንን ሐዋርያትን በትንቢት ጠሯቸው አነሷቸው ። ወሶበ ኃልቀ ወይኖሙ ትቤሎ እሙ ስቴ ሕይወት ስቴ መድኃኒት ባለቀባቸው ጊዜ ጥበቡ ስቴ ሕይወት ስቴ መድኃኒት አልቆባቸዋልና ተሰቅዬ ስቴ ሕይወት ስቴ መድኃኒት ልሁናቸው አሰኘችው ወይቤላ ምንት ብየ ። አንች ሆይ ተሰቅለህ ስቴ ሕያወት ስቴ መድኃኒት ሁናቸው ብትዪኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ተሰቅዬ ስቴ ሕይወት ስቴ መድኃኒት ልሆናቸው ሰው ሁኛለሁ እንጂ ተሰቅዬ ስቴ ሕይወት ሰቴ መድኃኒት ላልሆናቸው ሰው ሆኛለሁ አላት ።

ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜየ ። ነገር ግን የምሰቀልበት ጊዜ አልደረሰም ። ጌታ የሚሰቀል ባራተኛው ፋሲካ ነውና ። ወትቤሎሙ እሙ ። ጥበቡ መምህራን ያዘዟችሁን ሁሉ ሥሩ አለቻቸው ወሀለዋ መሳብክት ስድስቱ ። በስድስተኛው ሺህ የነበረ ሰው ሁሉ አእምሮው እንደ ደንጊያ መፍዘዙን መናገር ነው ። ወያገምራ በበከልኤቱ ወበበሠለስቱ ። አንብብ መጻሕፍተ በበከልኤቱ ወበበሠለስቱ እንዲል ፡ በበከልኤቱ መጻሕፍተ ነቢያትን ወበበሠለስቱ መጻሕፍተ ሐዲሳትን መቀበላቸውን መናገር ነው ። ዐሥራ አምስት ባለው ዓሥርቱ ቃላትን አምስቱ አዕማደ ምሥጢርን መቀበላቸውን መናገር ነው ዐሥራ ስምንት ባለው ያሥራሁለቱን ሐዋርያት ትምህርት ስድስቱን ቃላት ። ዐሥራ ሁለት ባለው ያሥራሁለቱን ሐዋርያት ትምህርት መቀበላቸውን መናገር ነው ወይቤሎሙ ምልእዎን ፡ አስተምሯቸው አላቸው ። ወመልእዎን ፡ ፍጹም ትምህርት አስተማሯቸው። ወይቤሎሙ ቅድኅዎን ፡ምሳሌውን ስአብርሃም ንገሩት አላቸው ። ወወሰዱ ወወሀብዎ ፡ ነገሩት ። ወጥዒሞ አንከረ ። ምሳሌውን ሰምቶ አደነቀ ወኢያእመረ እምኀበ እምጽእዎ ። ካመጡበት ግን አላወቀም ። ወገዛእትሰ እለ ቀድኅዎ መምህራን ግን ያውቃሉ ። እስመ እሙንቱ መልኡ ገልጠላቸው አስተምረዋልና ። ወጸውዖ ሊቀ ምርፋቅ ። አብርሃም ጌታን ሰው ሁሉ ደገኛውን ሕግ አስቀድሞ ይሠራል ። ወእምድኅረ ሰክሩ ያን ከጠበቁ በኋላ ግን ተራውን ሕግ ይሠራል ቢጠበቁ ይጠብቁት ባይጠብቁ አያስጎዳም ብሎ ፡ ወአንተሰ ዘይሤኒ ወይነ ዓቀብከ ፡ አንተ ግን ደገኛውን ሕግ እስካሁን አቆየህ አንድም ፈጽመህ አቆየህ ። ወዝንቱ ቀዳሜ ተአምር ይህ አያስወጥም ።

ዘከመ ዐርገ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ።

፲፪ ወእምድኅረ ዝንቱ ወረዱ ቅፍርናሆም ውእቱ ወእሙ ወአኃዊሁ ወአርዳኢሁኒ ምስሌሁ ።

፲፪ ከዚህ በኋላ እርሱ እናቱም ደቀመዛሙርቱም ወደ ቅፍርናሆም ወረዱ ።
ወነበሩ ህየ ኅዳጠ መዋዕለ ።
ከዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ ። ወአኮ ብዙኃ ። ብዙም አይደለም የቁጥር መጽሐፍ ዐሥራ አንድ ቀን ይለዋል

፲፫ ወቀርበ በዓለ ፋሲካሆሙ ለአይሁድ ።

፲፫ አይሁድ ፋሲካን የሚያከብሩበት ቀን ደረሰ መጀመሪያ ፋሲካ ነው ፡ ጌታ የሚሰቀል ባራተኛው ፋሲካ ነውና ዮሐንስ ፋሲካውን ጠንቅቆ ይቈጥራል ወዓርገ እግዚእ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ።
ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ ።
ዘከመ ተሰዱ ሠየጥ እምኩራብ

፲፬ ወረከበ በምኵራብ እለ ይሠይጡ ወይሣየጡ አልሕምተ ወአባግዐ ወአርጋበ ወመወልጣነ እንዘ ይነብሩ ።

፲፬ በመቅደስ ላም በግ ርግብ የሚሸጡትን ተቀምጠው ማለት ገበያ አድርገው አገኘ ።

፲፭ ወገብረ መቅሠፍተ ጥብጣቤ ዘሐብል ።

፲፭ ዘሐዊን እለና ዘሐብል አለ ማሰሪያ አበጀ እርሱ አላበጀም ሐዋርያት አብጅተው

ሰጥተውታል የጭፍራውንም ላሊቃው ሰጥቶ መናገር ልማድ ነው ።

ወከመዝ ገብረ ሙሴ በዞሚር ወበአከሲኖዶስ እንዲል ።
ወሰደደ ኵሎ እምኵራብ አባግዐኒ ወአልሕምተኒ ።
ላሙን በጉን ሁሉ ከምኵራብ አስወጣ ማለት ገበያውን ፈታ ወዘረወ ወርቆሙ ለመወልጣን የለዋጮችን ገንዘባቸውን በተናባቸው ። የሰው ገንዘብ አታበላሹ ይል የለም ቢሉ ለሰውነታቸው ቤዛ ሁኑዋቸዋል ። ማዕስ ቤዛ ማዕስ እንዲል ። አንድም በተአምራት ገንዘብ ገንዘባቸውን ለይቶ ይሰጣቸዋል አንድም ከዛፍ ላይ እንደ ሰፈረ ንብ ከዕቃ ከዕቃቸው ላይ እየተጣበቀ ተገኝቷል ።

ወገፍትዓ ማዕዳቲሆሙ ።
ድርድራቸውን ሰፈራቸውን አፈረሰ ።
ወመናብርቲሆሙ ለእለ ይሠይጡ ርግበ ገንጸለ ።
ርግብ የሚሸጡትንም ፥ ወንበራቸውን ገለበጠባቸው ቋንጤ ወንበር አላቸው ከዚያ ሁነው ርግብ ይሸጣሉ የከተማ ቅሬ በወንበር ሁና ዶሮ እንድትሸጥ

፲፮ ወይቤሎሙ ለእለ ይሰይጡ ርግበ አሰስሉ ወአውፅኡ ዘንተ እምዝየ ።

፲፮ አንሡ አላቸው ርግቦች በትር አይችሉ ምና ።
ወኢትረስዩ ቤተ አቡየ ቤተ ምሥያጥ ።
ባባቴ ቤት ገበያ አታድርጉ ።

፲፯ ወተዘከሩ አርዳኢሁ ከመ ጽሑፍ ውእቱ ዘይብል ቅንዓተ ቤትከ በልዓኒ ። መዝ. ፷፰ ፥ ፲ ።

፲፯ ደቀ መዛሙርቱም የቤትህ ቅናት አቃጠለኝ የሚል ጽሑፍ እንዳለ አሰቡ ።

፲፰ ወአውሥእዎ አይሁድ ።
፲፰ አይሁድም መለሱ ።
ወይቤልዎ ምንተ ትእምርተ ታርኢ ዘዘንተ ትገብር ።
ይህን የምትሠራ ምን ምልክት ታሳያለህ ማለት ከምድራውያን ነገሥታት ከሌዋውያን ካህናት ወገን ያይደለህ ገበያ መፍታትን ማን አሰናብቶህ ነው አሉት ።

፲፱ ወአሥውአ እግዚእ ኢየሱስ
፲፱ ጌታም መለሰ ። ወይቤሎሙ
ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ። ማቴ. ፳፮ ፥ ፷፩ ። ማር ፥ ፲፬ ፥ ፶፰ ።
ይህን ቤት መቅደስ አፍርሱት ፥
ወበሣልስት ዕለት አነሥኦ ።
በሦስተኛው ቀን አንጸዋለሁ ።

፳ ወይቤልዎ አይሁድ በ፵ ወ፮ ዓመት ተሐንጸ ዝንቱ ቤተ መቅደስ ።
፳ ይህ ቤተ መቅደስ በአርባ ስድት ዓመት ተሠርቶ ነበር ።

ወአንተሰ በሠሉስ መዋዕል ታነሥኦ ።
አንተስ በጉ በሦስተኛው ቀን አንጸዋለሁ አልክ ምን ይዘው እንዲህ አሉ ቢሉ ትሩፋን በባቢሎን ሳሉ ይህ ሁሉ መከራ ባባቶቻችን የተደረገባቸው ቤተ መቅደስን ባያሠሩ እንጂ ነው ። እኛ ሚጠቱ ለተደረገልን እንደሆነ ቤት ሳንሠራ ዘር ሳንዘራ ቤተ መቅደስን እንሠራለን ብለው ብፅዓት ገቡ ። ኋላ ሚጠቱ ተደረገላቸው ። ዘር ሲዘሩ ቤት ሲሠሩ ሁለት ዓመት ኑረዋል በሦስተኛው ጀምረው ባርባ ስድስት ዓመት ሠርተው ፈጽመዋል። ይህም በዘሩባቤል መንግሥት ይታወቃል የዘሩባቤል መላ ዘመነ መንግሥቱ አርባ ዘጠኝ ነው ። ሳይታነጽ ሁለት ዓመት ከታነጸ በኋላ አንድ ዓመት ኑሮ አርፏል ። አንድም ዘመን ያጠራጥራሉ መሥራት በጀመሩ በስድስተኛው ዓመት አጀም ኮንታ መጥተው አግቡን እናግራችሁ አሏቸው። አሪታቸው ኢያባእ ሞአባዊ ወአሞናዊ ትላለችና አይሆንም አሉአቸው ። ጽርእ ከአርጤክስስ ዘንድ ሂደው ነገር ሠሩባቸው ያች ሀገር አላዊተ ነገሥት ናት ልታምጽ ግንብ ትሠራለች ብለው ፥ አትሥሩ ብሎ ዐዋጅ ነገረባቸው ተጀምሮ ቀረ። ዓቢይ አርጤክስስ ሙቶ ካልዕ አርጤክስስ ነገሠ፡ በእናቱ አይሁዳዊ ነው የአርጤክስስ ልጅ ነው ከቃቤት ገብቶ ታሪክ ሲመለከት የቤተ መቅደስን ሥርዓት ሞዓብ አሞን መገበራቸውን አገኘ ። ዛሬ እንደምን ሁነዋል ብሎ ጠየቀ መሥራት ጀምረው ነበር አዋጅ ተነግሮባቸው ተጀምሮ ቀርቷል አሉት። ይሥሩ ሞዓብ አሞንም እንደጥንቱ ይገብሩላቸው ብሎ ዐዋጅ ነገረላቸው ሠላሳ ዘመን ሠርተው ጨርሰዋል ። ዐሥሩ ተየት ይመጣል ቢሉ ሄሮድስ ወልደ ሐንደፈር በእናቱ አይሁዳዊ ባባቱ አረማዊ ነው ለገቢረ በዓል ወጥቶ ሳለ ሠላሳ ስድስት ዓመት የሠሩትን አይቶ ባባቶቻችን ዘመን የተሠራው ደግ ነበር ይሉናል አላማረምሳ አላቸው አባቶቻችንማ ሞአብ አሞን እየገበሩላቸው በተድላ በደስታ ሁነው ነው የሠሩት እኛማ በግራ እጃችን ጋሻ ጦር በቀኝ እጃችን ጭቃ ደንጊያ እያቀበልን ነው የሠራነው አሉት ።

አፍርሼ ልሠራላችሁ አላቸው በእናቱ አይሁዳዊ ቢሆን ባባቱ አረማዊ ነው አፍርሶ ቢተውብንሳ ብለው ጠርጥረውት ዝም አሉ ። እሱም ዐውቆባቸው ጠርጥረውኝ እንጂ ነው ብሎ ስምንት ዓመት አዘጋጅቶ

በሁለት ዓመት ሁለት ዓመት አዘጋጅቶ በስምንት ዓመት ሠርቶ ጨርሶታል ።

፳፩ ወውእቱሰ በእንተ ቤተ ሥጋሁ ይቤሎሙ ፳፩ ስለ ሥጋው መቅደስ ማለት እሱ ግን ማኅደር ስለሚባል ሰውነቱ እንዲህ አላቸው ።

፳፪ ወአመ ተንሥአ እምነ ምውታን ተዘከሩ አርዳኢሁ ከመ በእንተዝ ይቤ ። መዝ ፷፰ ፡

፳፪ ከሙታን ተለይቶም ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ያላቸው ማኅደር ስለሚባለው ሰውነቱ እንደሆነ ዐወቁ ። ወሶበ ተንሥአ እምነ ምውታን ሶቤሃ ከሠተ ሎቱ አእመሩ ወሰበውወኮኑ ከመ ሰብል እንዲል እንደ ተደመጠ ብራና ሁነዋል ወአምኑ በቃለ መጻሕፍት ።

በመጻሕፍት ቃል አመኑ ። ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሕ እምንዋም ። ይትነሣእ እግዚአብሔር ወይዘረው ፀሩ ባለው ወበቃለ እግዚእ ኢየሱስ ዘይቤሎሙ ።

ጌታችን ኢየሱስ በተናገረውም ነገር ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ባለው ። አንድም ወቀርበ በዓለ ፋሲካሆሙ ለአይሁድ ብለህ መልስ ። አይሁድ የተባሉ ። ምእመናን ናቸው ። ጌታ ከሕይወት ወደ ሞት የሚሄድበት ምእመናንም ወደ ሕይወት የሚሄዱበት ዘመን በደረሰ ጊዜ ዓርገ እግዚእ ኢየሱስ ጌታ ተሰቀለ ፡ ኢየሩሳሌም ማለት ሀገረ ሰላም ማለት ነው ። ሀገረ ሰላምም የተባለ መስቀል ነው። ወረከበ በምኵራብ መሥዋዕተ ኦሪትን ሲሠው አገኘ ። ወመወልጣነ ። በኦሪት ሥርዓት የሚለውጡትን ። ወገብረ መቅሠፍተ ጥብጣቤ ሥልጣነ ክህነትን ኀንዘብ አደረገ ። ወሰደደ ኵሎ መሥዋዕተ ኦሪትን አሳለፈ ። ወዘረወ ወርቆሙ በኦሪት ሥርዓት ጸንተው ሥርዓት የሚለዋውጡትን ሕጋቸውን አሳለፋባቸው ። ወገፍትዓ ። ከልዕልናቸው አዋረዳቸው ከሹመታቸው ሻራቸው ።

ወይቤሎሙ ለእለ ይሰይጡ ርግበ መሥዋዕተ ኦሪት የሚሠውትን መሥዋዕተ ኦሪት አትሠው አላቸው ። ወኢትረስዩ ባባቴ ቤት መሥዋዕተ ኦሪት አትሠው ። ወተዘከሩ አርዳኢሁ ከመ ጽሑፍ በቤትህ የቀናሁት ቅናት እንደ እሳት አቃጠለኝ የሚል ጽሑፍ እንዳለ ደቀ መዛሙርቱ ዐወቁ ። ወአውሥእዎ አይሁድ ። አቡየ የምትል ምን ምልክት አለህ አሉት ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ይህንስ ብላችሁ ግደሉኝ አላቸው። እርሱስ እይዛቸውም እንዳይተውት ያውቃልና እንዲህ አለ እንጂ ። ወበሠሉስ ዕለት እነሥእ በሦስተኛው ቀን አሥነሣዋለሁ እፈጽመዋለሁ ። በ፵ወ፮ ዓመት ተሐንጸ ፡ ሥጋዌ በአርባ ስድስቱ ብሉያት ተነግሮ ነበር ፡ ወአንተሰ አንተስ በ፫ በሦስተኛው ቀን አሥነሣዋለሁ እፈጽመዋለሁ አልክ ። ወውእቱሰ እርሱም ማኅደር ስለሚባል ሰውነቱ ነው እንዲህ ያላቸው ወአመ ተንሥአ እምነ ምውታን ተዘከሩ እንዲህ ያላቸው ማኅደር ስለሚባል ሰውነቱ እንደ ሆነ ከተነሣ በኋላ ዐወቁ ፡ ወአምኑ በቃለ መጻሕፍት ቅንዓተ ቤትከ በልዓኒ ባለው አመኑ ፡ ወበቃለ እግዚእ እየሱስ ፡ እንዲህ ሲል ያውካል አቡየ ያለ ውንም ብታደርገው ይሆናል ።

በእንተ ቀዳሚት ፋሲካ ዘኢየሱስ ።

፳፫ ወእንዘ ሀሎ እግዚእ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም በበዓለ ፋሲካ ብዙኃን አምኑ ቦቱ ሶበ ርእዩ ተአምረ ዘገብረ ።

፳፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለበዓል ኢየሩሳሌም ወጥቶ ሳለ ያደረገውን ተአምራት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች አመኑበት ።

፳፬ ወውእቱሰ ኢየሱስ ኢየአምኖሙ

፳፬ እርሱ ግን አላመናቸውም ። ማለት እንዳመኑ ይቀራሉ አላለም ። ኢያየቀ ሎሙ ርእሶ ኢያግኃደ ሎሙ ርእሶ ኢከሠተ ሎሙ ርእሶ ይላል፡ እስመ የአምሮሙ በኵሉ ለለአሐዱ ። አንዱንም አንዱን ያውቀዋልና ።

፳፭ ወኢይፈቅድ ይንግርዎ ግዕዘ ለሰብእ ።

፳፭ የሰውን ግብሩን ሊነግሩት አይሻምና።

ወውእቱሰ የአምር ሕሊና ሰብእ እምቅድመ ኩነታ እንዲል ።
እስመ ለሊሁ የአምሮ ለሰብእ እርሱ ጥቂቱን በሰው ያለውን ሁሉ ያውቅ ነበርና ። እምቅድመ ይፍጥሮ ለአዳም የአምር ግብሮ እንዲል ።

በእንተ ኢየሱስ ወኒቆዲሞስ ።

ምዕራፍ ፫ ።

፩ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምፈሪሳውያን ዘስሙ ኒቆዲሞስ ።

፩ ብዙኃን አምኑ ቦቱ ብሎ ነበርና ፡ ብዙኃን ካላቸው ከፈሪሳውያን ወገን የሚሆን ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበር መልአኮሙ ለአይሁድ የአይሁድ አለቃ መልአኮሙ በትምርት በሹመት በባለጸግነት ።

፪ ወውእቱ መጽአ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ቀዲሙ ሌሊተ ።

፪ አስቀድሞ በሌሊት ወደ ጌታ የመጣ ለግንዘት መጣ የሚለው ነውና ከዚያ አስቀድሞ አንድም በመዓልት ከሚመጡት አስቀድሞ አንድም ከማመን አስቀድሞ በሌሊት አለ ውዳሴ ከንቱ ሽቶ መምህር ነኝ

እያለ እስከ ዛሬ ድረስ ትምህርት ሳይከታተል ኑሯል ይሉኛል ብሎ ። እንድም የቀን ልቡና ባከና ነው ። የሌሊት ልቡና ከት ነውና ትምህርት እንዲረዳው ። አንድም እመቦ ዘአምነ ቦቱ ከመ ከርስቶስ ይሰደድ እምኵራብ ብለው ዐዋጅ ነግረው ነበርና አይሁድን ስለፈራ ። ያም ሆነ ያም ሆነ ከግላ እራት እንዳልተላቀቀ በመንፈስ ቅዱስ እንዳልታወቀ ያጠይቃል ።

ወይቤሎ ረቢ ነአምር ከመ እምኀበ እግዚአብሔር መጻእከ ከመ ትኩን መምህረ ።

አላመነም ብሎ መምህር ከእግዚአብሔር ታዞህ ልታስተምር እንደመጣህ እናውቃለን። እስመ አልቦ ዘይክል ይግበር ዘንተ ተአምረ ዘአንተ ትገብር አንተ የምታደርገውን ተአምራት ሊያደርግ የሚቻለው የለምና፣ አንደም ኢይክል አሐዱሂ ይላል አብነት አንዱ ስንኳን ሊያደርገው አይቻለውምና ። ዘእንበለ ዘእግዚአብሔር ምስሌሁ ።

እግዚአብሔር ካደረብህ ካንተ በቀር ። አንድም እምኑዋል ብሎ መምህር ከእግዚአብሔር አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልደህ ልታስተምር እንደመጣህ እናውቃለን ። እስመ ዘይክል አንተ የምታደርገውን ተአምራት ሊያደርገው የሚቻለው የለምና ። ኢይክል አሐዱሂ ። አንዱ ስንኳን ሊያደርገው አይቻለውምና ። ዘእንበለሂ ዘእግዚአብሔር በሕልውናው ከርሱ ጋር ካለህ ካንተ በቀር ።

፫ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።

፫ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ አማን አማን እብለከ ዘኢተወልደ ዳግመ ኢይሬእያ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ። ዳግመኛ ያልተወለደ ሃይማኖትን አያውቃትም ብዬ እንዳያውቃት በውነት እነግራችኋለሁ።ሃይማኖት አይቀደምም ልጅነት አይከተልም ቢሉ ወአልቦ ዘይክል ብሂለ እግዚእ ኢየሱስ ዘእንበለ መንፈስ ቅዱስ ሳዕሌሁ እንዲል ። መጽናቱን መጉላቱን መገለጡን ሲያይ እንዲህ አለ እንጂ እውነት ነው ሃይማኖት ይቀድማል ልጅነት ይከተላል ። አንድም ዳግመኛ ካልተወለደ መንግሥተ ሰማይ አይወርስም ብዬ እንዳይወርስ በውነት እነግርሃለሁ ። ያልተካከለ ዳግመ ነው ለልደተ ሥጋው ልደተ ነፍሱን ዳግመ አለው ። አንድም የተካከለ ዳግመ ነው ። ልደተ ነፍሱን ለልደተ ነፍሱ ዳግመ አለው ።

፬ ወይቤሎ ኒቆዲሞስ እፎ ይክል ብእሲ ዳግመ ተወልዶ እምድኅረ ልሕቀ ።

፬ ኒቆዲሞስም ካደገ በኋላ ሁለተኛ መወለድ ለሰው እንደምን ይቻለዋል አለው ።

ይክልኑ በዊአ ወገቢአ ውስተ ከርሠ እሙ ወይትወለድ ዳግመ ።

ሁለተኛማ ይወለድ ዘንድ ወደ አባቱ አብራክ ወደ እናቱ ማኅፀን መግባት ይቻለዋልን አንድም ይገባዋልን ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ጌታም መለሰ።

፭ ወይቤሎ አማን አማን እብለከ ዘኢተወልደ ዳግመ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ ኢይክል በዊአ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፭ ልደቱን ነግሮት መወለጃውን አልነገረውም ነበርና ሁለተኛ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ካልተወለደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይቻለውም ብዬ እንዳይቻለው በውነት እነግርሃለሁ ።

ሦስትነቱን በዚህ ነገረው ፣ እማይ ብሎ ወልድን እመንፈስ ቅዱስ ብሎ መንፈስ ቅዱስን ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር ብሎ እግዚአብሔር አብን ።

፮ እስመ ዘተወልደ እምሥጋ ሥጋ ውእቱ ።
፮ ከግዙፍ ሥጋ የሚወለድ ግዙፍ ነውና ይክልኑ ላለው ወዘተወልደ እመንፈስ መንፈስ ውእቱ ።

ከረቂቅ መንፈስ ቅዱስ የምትወለድ ነፍስ ረቂቅ ናትና እመንፈስ ላለው ።

፯ ወበእንተዝ ኢታንክር እስመ እቤለከ ሀለወክሙ ትትወለዱ ዳግመ ።

፯ ሁለተኛ ትወለዱ ዘንድ አላችሁ ስላልኩህ አታድንቅ ። አንድም እንድታደንቅስ ግዱን ትወለዱ ዘንድ አላችሁ ።

፰ እስመ መንፈስ ኀበ ፈቀደ ይነፍሕ ።
፰ ነፋስ በወደደው ይነፍሳል ።

ፈቀደ ሲል አይመችም ግዕዛን የለውምና ።
ወቃሎ ትሰምዕ ፣
ባሕር ሲገሥጽ ዛፍ ሲያናውጽ ድምፁን ትሰማዋለህ ወኢተአምር እምኀበ ይመጽእ ወኀበሂ የሐውር ። የሚመጣበትን የሚሄድበትንም አታውቀውም ። በምሥራቅ ፯ በምዕራብ ፯ መሳክው አሉት በዚህ ይወጣል በዚህ ይገባል አትለውም ።
ከማሁኬ ውእቱ ኵሉ ዘይትወለድ እመንፈስ ቅዱስ ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለዱት ልደት እንዲህ ነው ። አንድም እስመ መንፈስ እያልክ መልስ መንፈስ ረድኤት በወደደው ያድራል ። ወቃሎ ትሰምዕ ። ትንቢት ሲያናግር ሉባዔ ሲያስቈጥር ትሰማዋለህ። ወኢተአምር ሀብተ ሙሴ በኢያሱ ። ሀብተ ኤልያስ በኤልሳዕ ሲያድር አታውቅም ። ከማሁኬ ። ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለዱትም ልደት እንዲህ ነው ።

እንድም መንፈስ ቅዱስ በወደደው ያድራል ወቃሎ ትሰምዕ ። ቋንቋ ሲያናግር ምሥጢር ሲያስተረጕም ትሰማዋለህ ። ወኢተአምር ከወዴያ አለ ከወዴህ የለም ከወዴህ ወዴየ ይሄዳል ከወዴህ አለ ከወዴያ የለም ከወዴህ ወዴያ ይሄዳል አትለውም ። ከማሁኬ ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለዱት ልደት አሁን እንደ ተናገርኩት ነው ።

፱ ወአውሥአ ኒቆዲሞስ ወይቤሎ ይትከሃል ዝንቱ ይኩን ።

፱ ኒቆዲሞስም እንዴህ መሆን እንደምን ይቻላል ብሎ መለሰ ነገሩ በረቀበት ።

፲ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፲ ጌታም መለሰ ።

ወይቤሎ አንተ ሊቆሙ ለእስራኤል ።
አንት የእስራኤል መምራቸው ነህ ።
ወዘንተ ነገረ ኢተአምር ፣
ነገር ግን ይህን ነገር አታውቅም ።
ሊቆሙ ብሎ ማለምለም ። ኢተአምር ብሎ መገሠጽ
እንድም የእስራኤል መምህር ያታውቅ ።

፲፩ አማን አማን እብለከ ከመ ዘነአምር ንነግር ።

፲፩ ራሱን ከዮሐንስ አግብቶ ያየነውን የሰማነውን እናስተምራለን ብዬ እንድናስተምር በውነት እነግርሃለሁ ።
ወስምዓነሰ ተአብዩነ ነሢአ ፣
ምስክርነታችንን ግን አትቀበሉንም ።

፲፪ ሶበ እንዘ ዘበምድር እነግረክሙ ኢተአምኑኒ ወእፎ እንከ ተአምኑኒ እመ ነገርኩክሙ ዘበሰማያት ።

፲፪ ምድራዊ ልደታችሁን ስነግራችሁ ብነግራችሁ ያልተቀበላችሁኝ ሰማያዊ ልደታችሁን ብነግራችሁ እንደምን ትቀበሉኛላችሁ ለዚህ ምክንያት አለው በጥምቀት በንፍሐት ይሰጣል ። ለዚያ ግን ንቃሕ ዘትነውም ባለው ነው ምክንያት የለውምና።

፲፫ ወአልቦ ዘዓርገ ውስተ ሰማይ ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።

፲፫ ወደሰማይ የወጣ የለም ወደ ሰማይ የወጣው ከሰማይ የወረደው ክርስቶስ ነው እንጂ ይኸንስ ለምን ይሻዋል ቢሉ የወጣውም የወረደውም አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው ለማለት ። እንድም አማን አማን እብለከ ብለህ መልስ። ራሱን ከአብ ጋራ አንድ አድርጎ በሀልውና ያየነውን በሀልውና የሰማነውን እናስተምራለን ብዬ እንድናስተምር በውነት እነግራችኋለሁ ወስምዓነሰ ምስክርነታችንን ግን አትቀበሉትም ። ወሶበ እንዘ በምድር ምድራዊ ልደቴን ብነግራችሁ ስነግራችሁ ያልተቀበላችሁኝ ሰማያዊ ልደቴን ብነግራችሁ እንደምን ትቀበሉኛላችሁ ። ሁሉስ አንድ አይደለምን ቢሉ ይህ ምክንያት አለው ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ሰው ሁሉ ያየዋል ሰው ሲሆን ያየው የለምና ። በአምሳለ ሊቀ መላእክት ታየኋቸው እስከ ሣልስ ሰማይ ሸኙኝ ይል የለምን ቢሉ መዳረሻው ስለ አልታወቀ ።
ወአልቦ ዘዓርገ ውስተ ሰማይ ሰማያዊ ሀብትን ሰማያዊ ዕውቀትን ገንዘብ ያደረገ የለም ።
ዘእንበለ ሰማያዊ ሀብትን ሰማያዊ ዕውቀትን ገንዘብ ያደረገ ከሰማይ የወረደው ክርስቶስ ነው እንጂ ።

፲፬ ወበከመ ሙሴ ሰቀሎ ለአርዌ ምድር በገዳም ። አሪት ዘኁ. ፳፩ ፡ ፱

፲፬ ሙሴ እባብ በምድረ በዳ እንደሰቀለ ። ከማሁ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ይሰቀል የሰው ልጅ ክርስቶስ ይሰቀል ዘንድ አለው ። ጌታ መሰቀሉ ስለምን ነው ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊደርስ ሊፈጸም ። ትንቢት ስቅለተ ትሬእያ እሥራኤል ለሕይወትከ ወኢትትአመና ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም ጌታ እሥራኤልን ከደመና መና አውርዶ ከጭንጫ ውኀ አፍልቆ ቢመግባቸው ከዚህ ምድሩ ብቅ ሰማዩ ዝቅ ቢልለት ከደጋ ላይ ቢሆንለት የውርጭ ሰደቃ እያበጀ ውኀውን እያረጋ መና መገብኳችሁ ይላል እንጂ ይከልኑ እግዚአብሔር ሠሪዓ ማዕድ በገዳም ። ቆላ በሆነማ ባልተቻለውም ነበር ብለዋል ጌታም የርሱን ከሃሊነት የርሳቸውን ሐሰት ለመግለጥ ሙሴን አውርዶሙ ቆላተ ሐራሴቦን አለው ነቅዓ ማይ የሌለበት በረሃ ነው ይዟቸው ወርዷል መናም ዘንሞላቸዋል ወኀውም ፈልቆላቸዋል ። ነገር ግን ነዘር የሚባል እባብ እየነከሰ ይፈጃቸው ጀመረ ሙሴን ከኛ ስሕተት ኃጢአት አይታጣምና ወደ እግዚአብሔር አመልክትልን አማልደን አሉት ወደ እግዚአብሔር ቢያመለከትላቸው ጽሩዩን ብርት አርዌ አስመስለህ ሠርተህ አንብር ሎሙ ኀበ ኵሉ ይትዔመሩ ከሚገናኙበት ዐደባባይ ከዕንጨት ላይ ስቀልላቸው ያልጸናባቸው መልኩን እይተው የጸናባቸው ድምፁን ብቻ ሰምተው ይዳኑ አለው እንዳዘዘው አደረገው ያልጸናባቸው መልኩን እይተው የጸናባቸው ድምፁን ብቻ ሰምተው ድነዋል ። አርዌ ምድር የዲያብሎስ አርዌ ብርት የጌታ ምሳሌ በአርዌ ምድር መርዝ እንዳለበት በዲያብሎስ ፍዳ ኃጢአት አለበት ። በአርዌ ብርት መርዝ እንደሌለበት በጌታም ፍዳ ኃጢአት የለበትም ጽሩይ እንደሆነ ጌታም ጽሩየ ባሕርይ ነው ። አርዌ ብርት በአርዌ ምድር አምሳል መሰቀሉ ጌታም በአርአያ እኩያን ለመሰቀሉ ምሳሌ ተኊለቈ ምስለ ጊጉያን

እንዲል ። ይኸንም ሊቁ ከመ ይደምረነ ምስለ ነፍሰ ጻድቃን ብሎ ተርጉሞታል መልኩን አይተው ድምፁን ሰምተው የዳኑ ከቃሉ ሰምተው ያመኑ የዳኑ ድምፁን ብቻ ሰምተው የዳኑ ከርሱ በኋላ ከተነሡ መምህራን ሰምተው ያመኑ የዳኑ የምእመናን ምሳሌ

፲፭ ከመ ኵሉ ዘአምነ ቦቱ ኢይትኃጐል ።
፲፭ በርሱ ያመነ ሁሉ እንዳይጎዳ አላ ይሕየው ሕይወተ ዘለዓለም ።

ለዘለዓለም ይድን ዘንድ እንጂ አንድም አይጐዳም አላ የሐዩ ይድናል እንጂ ።

፲፮ እስመ ከመዝ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም እስከ ወልዶ ዋሕደ መጠወ ወወሀበ ቤዛ ኵሉ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፱ ።

፲፮ አንድ ልጁን ለሁሉ ቤዛ አድርጎ እስከ መስጠት ደርሶ እግዚአብሔር ዓለሙን ወዶታልና። ከመ ኵሉ ዘየአምን ቦቱ ኢይትኃጐል ።

በርሱ ያመኑ ሁሉ እንዳይጐዱ አላ ይረከብ ሕይወተ ዘለዓለም፥ የዘላለም ደህንነት ያገኝ ዘንድ ነው እንጂ አንድም በርሱ ያመነ ሁሉ አይጐዳም ። አላ ይረክብ ። የዘላለም ደኅንነት ያገኛል እንጂ ።

፲፯ እስመ ኢፈነዎ እግዚአብሔር ለወልዱ ውስተ ዓለም ከመ ይኰንኖ ለዓለም ።

፲፯ እግዚአብሔር በዓለሙ ሊፈርድበት ልጁን ወደዚህ ዓለም አልሰደደውም ።

ዘእንበለ ከመ ያሕይዎ ለዓለም በእንቲአሁ ። እርሱ ስለ ካሰለት ያድነው ዘንድ እንጂ ። አንድም አስቀድሞ ያልተፈረደበት ሁኖ ሊፈርድበት አልሰደደውም ዘእንበለ ከመ ያሕይዎ ። ተፈርዶበታልና ከተፈረበት ፍርድ ሊያድነው ነው እንጂ አንድም በሥጋው ሊፈርድበት አላከውምና እጅ ለሌለው እጅ እግር ለሌለው እግር ። ዓይን ለሌለው ዓይን ሊሰጠው ነው እንጅ ።አንድም በመንፈሳዊው ቅሉ ሊፈርድበት አልሰደደውም ተኃድገ ለኪ ኃጢአትኪ ተኃድገ ለከ ኃጢአትከ እያለ ስርየተ ኃጢአትን ሊሰጥ ነው እንጂ ።

፲፰ ዘየአምን ቦቱ ኢይትኴነን ።
፲፰ በርሱ ያመነ አይፈረድበትም ወዘሰ ኢአ

ምነ ቦቱ ወድአ ተኰነነ በርሱ ባላመነ ግን ፈጽሞ ይፈረድበታል ።

እስመ ኢአምነ በስመ ወልደ እግዚአብሔር ዋሕድ ባንድ በእግዚአብሔር ልጅ አላመነምና ዋሕድ ለሁሉቱም ቅጽል ።

፲፱ ወዝውእቱ ኵነኔሁ ። ዮሐ ፡ ፩፥ ፱
፲፱ ፍርዱም ይህ ነው ።

እስመ ብርሃን መጽአ ውስተ ዓለም ።
ብርሃን ክርስቶስ ወደ ዓለም መጥቷልና ።
ወአብደረ ሰብእ ጽልመተ እምብርሃን ።
ሰውም ከብርሃን ጨለማን ከዕውቀት ድንቁርናን ከክርስቶስ ሰይጣንን ከወንጌል ኦሪትን ወዷልና ።
እስመ እኩይ ምግባሩ ።
ሥራው ከፉ ስለሆነ ።

፳ እስመ ኵሉ ዘእኩይ ምግባሩ ይጸልዕ ብርሃነ ።

፳ ምግባሩ ክፉ የሆነ ሰው ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና ።
ወኢይመጽእ ኀበ ብርሃን
ወደ ብርሃን አይመጣም ።
ከመ ኢይትከሠቶ ምግባሩ ።
ሥራው እንዳይገለጥበት እስመ እኩይ ውእቱ ሥራው ክፉ ስለሆነ ዓይነ ዘማዊ ይጸንሕ ጽልመተ ወያጼልል ዲበ ገጸ ማይ ያለውን ለውጦ አነበበው ።

፳፩ ወዘሰ ጽድቀ ይገብር ይመጽእ ኀበ ብርሃን
፳፩ ሥራው በጎ የሆነ ሰው ግን ወደ ብርሃን ይመጣል ።

ከመ ያስተርኢ ምግባሩ ።
ሥራው ይገለጥ ዘንድ ።
እስመ በእንተ እግዚአብሔር ይገብር ።
ለለ እግዚአብሔር ብሎ ይሠራዋል ። ማለት ሥራው በጐ ስለሆነ አንድም እስመ ኵሉ ዘእኩይ ምግባሩ እያልክ መልስ ሥራቸው ክፉ የሆነ ጸሐፍት ፈሪሳውያን አንድም ሥራቸው ክፉ የሆነ አይሁድ አንድም ሥራቸው ክፉ የሆነ አሕዛብ ጌታን ያጠላሉ ወኢይመጽእ ፡ በጌታ አያምኑም ከመ ኢይትከሠቶ ሥራቸው እንዳይገለጥ እስመ እኩይ ውእቱ ሥራቸው ክፉ ስለሆነ ወዘሰ ሥራቸው በጐ የሆነ ሐዋርያት አንድም ሥራቸው በጐ የሆነ አይሁድ አንድም ሥራቸው በጐ የሆነ አሕዛብ ግን በጌታ ያምናሉ ሥራቸው ይገለጥ ዘንድ ሥራቸው በጐ ስለሆነ ።

በእንተ ዳግማዊ ስምዑ ለዮሐንስ

፳፪ ወእምዝ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ ወአርዳኢሁ ምስሌሁ ውስተ ምድረ ይሁዳ ዮሐ. ፬ ፩ ።

፳፪ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መ ዛ ሙ ር ቱ ጋር ወደ ምድረ ይሁዳ ሄደ ። ወሀየ ነበረ ምስሌሆሙ እንዘ ያጠምቅ ።

በዚያም ከርሳቸው ጋራ ሲያጠምቅ ኖረ እርሱስ አላጠመቀም ወለሊሁሰ ኢያጥመቀ ብሎ ያመጣዋል የሐዋርያትን ስርሱ ሰጥቶ መናገር ነው እንጂ ። ወከመዝ ገብረ ሙሴ በዞሚር ወበአክሲኖዶስ እንዲል

፳፫ ወሀሎ ዮሐንስኒ ያጠምቅ በሄኖን በቅሩበ ሳሌም በማዕዶተ ዮርዳኖስ ።

፳፫ በ ና በ አንድ ወገን ዮሐንስም የሳሌም አቅራቢያ በምትሆን በሄኖን ያጠምቅ ነበር ። እስመ ቦቱ ሀየ ብዙኀ ማያት ብዙ የማዋት ውኀ ነበርና በከተማ አቅራቢያ መሆኑ ለዕውር ሳንካሳ እንዲመች ነው ።

ወይመጽኡ ኀቤሁ ብዙኃን ወያጠምቆሙ ።
ብዙ ሰዎች ወደርሱ እየመጡ ያጠምቃቸው ነበር

፳፬ እስመ ዓዲሁ ኢተወድየ ዮሐንስ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ።

፳፬ ዮሐንስ ገና አልተጋዘም ነበርና

፳፭ ወእምዝ ኮነ ተኃሥሦ ማእከለ አርዳኢሁ ለዮሐንስ ምስለ አይሁድ በእንተ አጥህሮ

፳፭ ከዚህ በኋላ አርድእተ ዮሐንስና አርድእተ ክርስቶስ በማጥመቅ ምክንያት በአይሁድ ዳኝነት ተከራከሩ ። ማጥመቅ የሚገባ ለኛ ነው እንጂ ለናንተ መቼ ይገባችኋል መምህራችሁ መስክሮ ለቆ የለም ብለው በአይሁድ ዳኝነት ይዘዋቸዋል ። አይሁድም ይህን ሰምተው እውነታቸው ነው ማጥመቅ የሚገባ ለኒህ ነው የናንተማ መምህር መስክሮ ለቆ የለም አሏቸው ። አይሁድ ይህን ያሉ እውነት ተናገርን ብለው አይደለም ዮሐንስ ይህን የሰማ እንደሆነ ተናዶ ነገር ይለውጥልናል ብለው ነው እንጂ ። አንድም አርድእተ ዮሐንስና አይሁድ በጥምቀት ምክንያት ተከራከሩ አርድእተ ዮሐንስ አይሁድን ወደ ጌታ ሲሄዱ አገኙዋቸው የኛ መምህር እያለ ወዴት ትሄዳላችሁ አሏቸው ማጥመቅ የሚገባ ለርሱ ነው እንጂ የናንተማ መምህር መስክሮ ለቆ የለም ብለዋቸው ሄዱ መጥተው ይህን ይነግሩታል ምክንያቱ እንዳለፈው ።

፳፮ ወሖሩ ኀበ ዮሐንስ ወይቤልዎ ዝኩ ዘምስሌከ ሀሎ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘአንተ ሰማዕተ ኮንከ በእንቲአሁ ናሁ ውእቱሂ ያጠምቅ ።

፳፮ ወደ ዮሐንስ ሄደው በዮርዳኖስ ማዶ ካንተ ጋራ የነበረ አንተ የመሰከርህለት ያ እነሆ ያጠምቅ ጀመር ብለው ነገሩት ።
ዝኩ ቃለ ጸብእ ነው ዝኩ ወልደ ዕሤይ እንዲል።
ወኵሉ የሐውር ኀቤሁ ።
ሰው ሁሉም ወደርሱ ይሄድ ጀመር አሉት።

፳፯ ወአውሥአ ዮሐንስ ወይቤ ኢይክል ሰብእ ነሢአ ጸጋ ለሊሁ ወኢምንትኒ እመ ኢተውህበ ሎቱ እምሰማይ ። ዮሐ ፩፥፲፱ ።

፳፯ ከሰማይ ካልተሰጠው ማለት ከእግዚአብሔር ካልተሰጠው መምህርነትን ገንዘብ ማድረግ ለሰው አይቻለውም ።

፳፰ አንትሙኒ ለሊክሙ ሰማዕትየ ከመ እቤለክሙ አንሰ ኢኮንኩ ክርስቶስሃ ።

፳፰ መሆኑንማ ክርስቶስ ነኝ እንዳላልኳችሁ እናንተም ቅሉ ምስክሮቼ ናችሁ ።
ዳዕሙ ተፈኖኩ ቅድሜሁ እስብክ ።
በፊቱ ተልኬአለሁ ማለት መንፈቅ ተቀድሜ ላስተምር ታዝዣለሁ እንጂ ።

፳፱ ዘቦቱ መርዓት መርዓዊ ውእቱ
፳፱ ሙሽራ ያለችው ሙሽራ ነው ማለት ያጨ እንጂ ያገባል ።
ወአርኩሰ ለመርዓዊ ዘይቀውም ወይሰምዖ ፍሥሐ ይትፌሣሕ በእንተ ቃለ መርዓዊ ወመርዓት ወፍሥሐ ዚአየሰ ናሁ ተፈጸመት ።

አርከ ላእክ ኀሩይ ይላል ግልገል መሪ ቀባጣሪ አማጭ ። የሙሽራና የሙሽራይቱ ነገር ሲወሰን ሰምቶ ደስ ይለዋል አንድም አልቦ ዘይክል ብለህ መልስ ። ከእግዚአብሔር ካልተሰጠው ሰማያዊ ዕውቀትን ገንዘብ ማድረግ ለሰው አይቻለውም።

፴ ወእንቲአሁሰ ትበዝኅ ወእንቲአየሰ ተሠልጠት ።

፴ የኔ መምህርነት አለፈች ተፈጸመች የሱ ግን አታልፍም አትፈጸምም ። አንተሙኒ ለሊክሙ ሰማዕትየ ። ነኝ እንዳላልኋችሁ እናንተ ቅሉ ምስክሮቼ ናችሁ ። ዳዕሙ ተፈኖኩ ላስተምር ታዘዝኩ እንጂ ። ዘቦቱ መርዓት ። ምእመናን ያሉት ክርስቶስ መምህር ነው ወአርኩሰ ለመርዓዊ ይትፌሣሕ በእንተ ቃለ መርአዊ ። የክርስቶስ ባለሟል የምሆን እኔ ክርስቶስ ሲያስተምር ምእመናን ትምርቱን ሲቀበሉት ሰምቼ ሲያድርባቸው ሲዋሐዳቸው አይቼ ደስ ይለኛል ። ወፍሥሐ ዚአየሰ ናሁ ኃልቀት ወተፈጸመት የኔ መምህርነት መንፈቅ ነበረች አለፈች ተፈጸመች ። ወእንቲአሁሰ ትበዝኅ የርሱ ግን መምህርነቱ አትፈጸምም ። ወእንቲአየሰ ተሠልጠት ። የኔ የተሰጠችኝ መንፈቅ ነበረች ያችውም ተፈጸመች ።

፴፩ እስመ እምላዕሉ መጽአ መልዕልተ ኵሉ ውእቱ ።

፴፩ ከሰማይ የመጣ እርሱ ከሁሉ በላይ ነው ። ማለት የባሕርይ አምላክ ነውና ። ትበዝኅ ።

ወዘእምድርሰ ምድራዊ ውእቱ ወዘበምድር ይነግር ።
ከምድር የተገኘሁ እኔ ግን ምድራዊ ነኝና የምድራዊን ነገር አስተምራለሁ ። ማለት ዘካርያስ አባቴ ኤልሳቤጥ እናቴ እያልኩ አስተምራለሁ ።
ወዘእምሰማይ መጽአ መልዕልተ ኵሉ ውእቱ ።

ከሰማይ የመጣ እሱ ግን የባሕርይ እምላክ ነው ።

፴፪ ወበዘርአየ ወበዘሰምዓ ስማዕተ ይከውን

፴፪ በሀልውና ያየውን ያስተምራል
ወስምዖሰ አልቦ ዘይትዌክፎ
ምስክርነቱን ግን የሚቀበለው የለም ።

፴፫ ወለዘሰ ተወክፎ ስምዖ ዓተበ እግዚ አብሔር ። ሮሜ ፫፥ ፬ ።

፴፫ ባይቀበሉትስ ምን ይጐዳል ቢቀበሉትስ ምን ይጠቅማል ትሉኝ እንደሆነ የተቀበለውንስ እግዚአብሔር አተመው ማለት ራሱን አስመስሎታል ።

እስመ ጻድቅ ውእቱ ።
እውነተኛ ማለት የባሕርይ አምላክ ነውና ።

፴፬ ወዘእግዚአብሔር ፈነዎ ቃለ እግዚአብሔር ይነግር ።

፴፬ እግዚአብሔር የሾመው እውነተኛ መምህርም የእግዚአብሔርን ነገር ያስተምራል ።
እስመ አኮ በመሥፈርት ዘይሁብ እግዚአብሔር መንፈሶ ።

እግዚአብሔር ስጭነት ተከፍሎበት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በልክ የሚሰጠው አይደለምና አተቦ። አንድም ወለዘሰ ተወክፎ ስምዖ ብለህ መልስ ባይቀበሉትስ ምን ይጐዳል ቢቀበሉትስ ምን ይጠቅማል ትሉኝ እንደሆነ የተቀበለውንስ ከኢአማንያን ለየው ። እስመ ጻድቅ እውነተኛ መምህር ነውና ወዘእግዚአብሔር ፈነዎ ቃለ እግዚአብሔር ይነግር ከእግዚአብሔር አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልዶ የመጣ እሱን የእግዚአብሔርነቱን ነገር ያስተምራል ። እስመ አኮ በመሥፈርት ። ሀብተ መንፈስን በልክ የሚሰጥ አይደለምና ።

፴፭ አብሰ ያፈቅር ወልዶ ወኵሎ ኵነኔሁ አወፈዮ ውስተ እዴሁ

፴፭ አብ ልጁን ይወደዋልና ሁሉን በጁ ጭብጥ በእግሩ እርግጥ አድርጐ አስገዛለት ።

፴፮ ዘየአምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም
፴፮ በወልድ ያመነ የማታልፍ መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል ። ፩.ዮሐ ፭ ፥ ፩ ።

ወዘሰ ኢየአምን በወልድ ኢይሬእያ ለሕይወት ዘለዓለም ።

በወልድ ያላመነ ግን የማታልፍ መንግሥተ ሰማይን አይወርስም ።
አላ መቅሠፍተ መዓቱ ለእግዚአብሔር ይነብር ላዕሌሁ ።

የእግዚአብሔር የቁጣው መቅሠፍት ማለት ፈርዶ ያመጣበትን ፍዳ ሲቀበል ይኖራል እንጂ ።

በእንተ ኢየሱስ ወሳምራዊት ።

ምዕራፍ ። ፬

፩ ወአአሚሮ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ሰምዑ ፈሪሳውያን ከመ በዝኁ አርዳኢሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ወአብዝኁ አጥምቆ እምዮሐንስ ።

፩ አርድእተ ክርስቶስ ከአርድእተ ዮሐንስ እንደበዙ ። ከአርድእተ ዮሐንስ አርድእተ ክርስቶስ አብዝተው እንዳጠመቁ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ሰምተው እንዳዘኑ ዐውቆ ።

፪ ወባሕቱ ለሊሁ እግዚእ ኢየሱስ ኢያጠምቅ ዳዕሙ አርዳኢሁ ።

፪ ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ ናቸው እንጂ እሱ አላጠመቀም

፫ ወኀደጋ ለምድረ ይሁዳ ወሖረ ካዕበ ገሊላ።
፫ የይሁዳን አገር ትቶ ሁለተኛ ወደገሊላ ሄደ ሰው የሚጠላባችሁን ሥራ አትሥሩ አትጠናቀሉ ለማለት አብነት ለመሆን ።

፬ ወእንዘ ሀለዎ ይኀልፍ እንተ ሰማርያ ።
፬ ሰማርያን ተረግጦ በሰማርያ በኩል ይሄድ ዘንድ ሳለው ።

፭ ወበጽሐ ሀገረ ሳምር እንተ ስማ ሲካር ዘፍ. ፴፫ ፥ ፲፱ ፡ ዘሌ. ፳፬ ፥ ፴፪ ።

፭ ሰማርያ ደረሰ ፡ ሐተታ ፍርቃን ተረግጦ በፍርቃ በኩል በጌምድር ይሄድ ዘንድ ሳለው ፍርቃ ደረሰ እንደማለት ።

ሴምር ይለዋል ። ለዘንበሪ በሁለት መቶ ብር ሸጦለታል ዋጋ አነሰኝ አለው በስምህ ትጠራልህ አለው በሱ ስም ሰማርያ ተብላለች ።
ታሪክ ለኤርምያስ ባሮክ አቤሜሌክ የሚባሉ ደቀ መዛሙርት ነበሩት ፣ የጼዋዌን ነገር ሲናገር እየሰሙ ኢታርእየነ ሙስናሃ ለኢየሩሳሌም እያሉ ሲጸልዩ ይኖሩ ነበር ። ጼዋዌ በደረሰ ጊዜ ፡ ጌታ ኤርምያስን ባሮክን መቃብረ ነገሥት አስጠብቀው አቤሜሌክን ለድውያን የምንቀባው ዕጽቀ በለስ ቆርጠህ አምጣ በለው አለው ። እንዳዘዘው እደረገ በዚህ ጊዜ እስራኤል ተማርከው ባቢሎን ወረዱ፣ አቤሜሌክም ዕጽቀ በለሱን ቆርጦ በሙዳይ አድድርጎ በሚሄድበት ጊዜ ቀትር ነበርና ዋዕይ ተሰማው ከዛፍ ሥር ከጥላ ዐረፈ ፡ ዕንቅልፍ መጥቶበት ተኛ ለተኛበት ሰዓት ጊዜ ገጥሞት ጥቂት እልፍ ብሎ ነቃ ዘግይቻለሁ መምህሬ ይቆጣኛል

ብሎ መንገድ ጀመረ መንገዱ ጠፍቶ አገሩ ተፈቶ የማያስሄደው ሆነ ዕንቅልፉስ ባይለቀኝ ነው ወይስ አእምሮዬ ተነሥቶኛል እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ አንድ አረጋዊ ታየው ፡ አገር በጠፋ በ፸፮ ዘመን ሰው የለም ተመትሯል ብሎ መልአክ በአምሳለ አረጋዊ ተገልጦለታል ። ሄዶ የናፍቆት አነጋገር አይቴ ሀለዉ ኤርምያስ ወአኃውየ መምህሬ ኤርምያስ ወንድሞቼ እስራኤል የት ነው ያሉ አለው ። አንተኑ ነግድ ለኢየሩሳሌም እነ ኤርምያስ ያሉ ፋርስ ባቢሎን በስደት ። ኢየሩሳሌም ከተፈታች ፸፮ ዓመት አንተ ለኢየሩሳሌም እንግዳ ነህ አለው ። አረት አክብር ገጸ አረጋዊ ባትል ይህ ጅጁ አእምሮውን ያጣ ሽማግሌ ብዬ በሰደብኩህ ነበር ። እነሆ መምህሬ ኤርምያስ ለደውያን የምንቀባው ዕጽቀ በለስ ቆርጠህ አምጣ ብሎኝ ደሟ ይንጠፈጠፋል ። ቅጠሏ አልጠወለገም ። አለው እስኪ አሳየኝ አለው ።

ቢያይ ደምዋ እየተንጠፈጠፈ ቅጠሏ ሳይጠወልግ አየ ። ሳንተ ተአምራት ቢደረግልህ ነው እንጂ ሲልከህ ምን ወራት ኑሯል አለው ። ወርኃ ዘርዕ ነው ቢለው ወርኃ ጽጌ ሁኖብሃልሳ ይለዋል ወርኃ ጽጌ ነው ቢለው ወርኃ ዘርዕ ሁኖብሃልሳ ይለዋል ። ነገሩን በዚህ ይረዳዋል ፡ ይልቅስ ና ከወንድምህ ክባሮክ ሳገናኝህ ብሎ ወስዶ አገናኘው ። የሚጠትን ነገር ግለጥልን ብለው ቀኖና ቢገቡ አራት አመት እንደ ቀረው ተገለጠላቸውዘ ወረቅት ጽፈው ማን በወሰደልን ሲሉ የታዘ። ንስር ቀረበ ። ወረቀቱን ከአንገቱ አስረው ዕጽቀ በለሱን ጨምረው ሰደዱት ። ኤርምያስም ከወገኑ ሰው ሙቶበት ከንጉሡ መቃብር ተካሶ ሊያስቀብር ሲሄድ ከፈረስ ግምብ ሥር አሳርፎ ሳለ ኤርምያስ ኤርምያስ ብሎ በቃለ ሰብአዊ ጠርቶ ወረቀቱን ጣለለት ። ወዲያው ወኬዶ ለምውት በእገሪሁ ይላል ምውቱን ቢረግጠው ተነሥቶ የወረቀቱን ቃል መስክሮ ዐርፏል ። ቃሉም ለሚጠት ፬ ዓመት ቀርቶታልና የተጋባችሁ ተፋቱ ያልተጋባችሁ ተጠበቁ የሚል ነው ከፋዎቹ ማን ሚጠቱ ይደረግ እንጂ አገራችንን ማን ነሥቶን ሚስታችንንስ ማን አፋቶን ብለው ዝም ብለው ኖሩ ። ጊዜው ቢደርስ ኤርምያስ ደጋጉቹን ይዞ ጉዞ ጀመረ እኒያም ተከተሉት አትከተሉኝ አትምጡብኝ ቀድሞ እንዲህ ብላችሁ አይሆንም ብላችኋል አላቸው ፡ አሕዛብም እንዴህ ሲጠሏችሁ አትቀሩም የሚስት የልጅ አገርስ አገር አይደለምን አሏቸው ፡ ሳንገባስ አንቀርም አይሆንም ብለው ሄዱ ። ፈለገ ኤፍራጥስ ሲደርሱ ባሮክን አቤሜሌክን አስረድቶ ገጠማቸው ። ድል አድርጎ ሰደዳቸው ተመልሰው ወደነበሩበት ሄዱ እንግዴህ ወዴህስ አትምጡብን አይሆንም ስንላችሁ እምቢ ብላችሁ ሄዳችኋል ። የወደዱትን ቢያጡ ያጡትን ይቀላውጡ እንዲሉ ፡ ብለው ሰደዷቸው እግራቸው እንዳደረሳቸው ሄደው አገር አቅንተው ኑረዋል ። ሠመርናሃ ብለዋታል ስለ ዚህ ሰማርያ ተብላለች ብዙ ስም አላት ሰማርያ ሲካር ቀራንዮ ሎዛ ቴምናስራህ ቤቴል ሰቂማ ወለምንሀሳ ተብላለች

፭ ቅሩበ ዐጸደ ወይን ዘወሀቦ ያዕቆብ ለዮሴፍ ወልዱ ።

፭ ዛቲ ሀብት እንተ ተዓቢ እምሀብት ዘነ ማእከዋ በቀስትየ ብሎ ያዕቆብ በበረከት ጊዜ ለልጁ ለዮሴፍ ለሰጠው ለወይኑ ቦታ አቅራቢያ የምትሆን ። ወወፅአት ዲና እንተ ተወልደት ሎቱ ለያዕቆብ ከመ ትርአይ አዋልደ ውእቱ ብሔር ይላል ባሥራሁለቱ መካከል የተወለደች የዛብሎን መንትያ ናት አሕዛብ መልክ መልካሞች ናቸው ዘፈን ያውቃሉና ልታይ ወጥታ ሳለች የሀገረ ገዢው ልጅ ነጥቆ ወስዶ ከክብር አሳነሳት ወአፍቀራ በነፍስታ ይላል ። ግዝርት ናትና መልክ መልካም ናትና ከቤት አኑሯት ሥርዓት ከጉልበት አባቴ ይህችን ብላቴና ወድጃታለሁና ተናገርልኝ አለው ። ሄዶ ለያዕቆብ ሴኬም ወልድየ አፍቀራ ለወለትክሙ ሀብዎ ከመ ትኩኖ ብእሲተ አለው ልጆቼ የሉም ሲመጡ መክሬ እነግርሃለሁ አለው ። መጡ ነገራቸው ፡ ነገራቸውን በልባቸው አድርገው እኛ ግዙራን እነሱ ቆላፋን ግዙራን ከቆላፋን ጋራ መጋባት እንደምን ይሆናል ተገዘሩ በላቸው አሉት በግዝረት ምስሉን አለው እርሱም እኒህ ሰዎች ገንዘብ ያላቸው ናቸው ኦሳ ቀድመን በግዝረት እንምስላቸው ከዚያ በኋላ እኛ በውራጃ እርሳቸው በግምጃ አንድ ሁነን የነኛን ሴቶች ልጆች ከእርሳቸው ወንዶች ልጆች የርሳቸውን ወንዶች ልጆች ከኛ ሴቶች ልጆች አጋብተን እንኖራለን አላቸው ። ያገሩም ሰዎች ተገዘሩ ።

ወእንዘ ጽሉአን እሙንቱ ይላል ቁስል የሚጸና በሦስተኛው ቀን ነውና ፡ ስምዖን ወሌዊ ቦኡ ተጋቢኦሙ ይላል ። ስምዖንና ሌዊ አይዞህ አይዞህ ተባብለው አፍ አፋቸውን ይዘው አርደው አርደው ፈጅተዋቸው እኅታቸውን ይዘው ወጥተዋል እስራኤል ጥቃት አይወዱምና ። ያዕቆብም ይህን ሰምቶ ደቂቅየ ለምንተ ከመዝ ረሰይክሙኒ ወአጽላእክሙኒ በኀበ ኵሉ ብሔር ውሑድ አነ በኍልቍየ ዳዕሙ እትቀጠቀጥ አነ ወቤትየ ብሏል፡ እንዲህ ስላለ በአሕዛብ ፍርሃት አድሮባቸው በጠ

ላትንት የተነሣባቸው የለም ።
ወሀሎ ህየ ዓዘቅተ ማየ ዘያዕቆብ ።
ከዚያ የያዕቆብ የውኅ ቦታ ነበር በመቶ በግ የዋጀው ። አንድም ለራሱ ብሎ ያስቆፈረው ወደኪሞ እግዚእ ኢየሱስ በሐዊረ ፍኖት ነበረ ፀየ ኀበ ውእቱ ዓዘቅት ።

ጌታችን መንገድ በመሄድ በደከመ ጊዜ ከዚያ ውኅ ዳር ዐረፈ ። በነጋዲያን ልማድ ጠል ለማንሣት። አንድም ሳምራዊትን አሳመን የሚለው ነውና ፤ ወቅትር ሶቤሃ ጊዜ ስሱ ሰዓት ያውም ድልድል ቀትር ነበር ቀትር ሲሆን ዋዕይ ይጸናል ከናላ ላይ ይወድቃል ሐሞት ይበትናል ሰውነት ይዝላልና ። ፮ም ሳምራዊት ውኅ ልትቀዳ መጣች የሚል ነውና ውኅ የሚቀዱበት ሰዓት ስዓት አላቸው ኢያውብርን በሠርክ አገኘ ይሉዋል ፤ ሳኦልን በሠለስት አገኘ ይሉዋል ወረከብኩ አዋልደ ይወፅአ ሐዋርያተ ማይ እንዲል ።

፯ ወናሁ መጽአት ብእሲት እምሰማርያ ከመ ትቅዳኅ ማየ ።

፯ አንዲት ሴት ውኅ ልትቀዳ ከሰማርያ መጣች ወይቤላ ኢየሱስ አስተዩኒ ማየ ውኅ አጠጭኝ አላት ።

፰ እስመ አርዳኢሁስ ሖሩ ሀገረ ከመ ይሳይጡ ኅብስተ ሲሳዮሙ

፰ ደቀ መዛሙርቱ ምግባቸውን እንጀራ ሊገዙ ወደ አገር ገብተው ነበርና ፤ አስትዩኒ ። አንድም ደቀ መዛሙርቱስ ትሉኝ እንደሆነ ደቀ መዛሙርቱስ ምግባቸውን ሊገዙ ወደ ሀገር ሄደው ነበር ።

፱ ወትቤሎ ይእቲ ሳምራዊት እፎኑ እንዘ አይሁዳዊ አንተ ትስእል እምኀቤየ ትስትይ ማየ እንዘ ሳምራዊት አነ ።

፱ ያችም የሰማርያ ሴት እንዴት አንተ አይሁዳዊ እኔ ሳምራዊት ስሆን ውኅ አጠጭን ትላለህ አለችው ። አንድም እፎ ትስእል ፤ አንተ አይሁዳዊ እኔ ሳምራዊት ስሆን እንደምን ውኅ አጠጭኝ ትላለህ አለችው ። በምን ዐውቃ እንዲህ አለች ቢሉ ባነጋገሩ ባጠማጠሙ ።

እስመ ኢየኀብሩ ሕርመተ አይሁድ ምስለ ሳምራውያን ።

አይሁድ ከሳምራውያን ጋራ በሥርዓት አንድ አይሆኑም ነበርና ።
ወኢይትሀወሉ ። በበዓል
ወኢይደመሩ ።
በግቢ አንድ አይደሉምና ።

፲ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ
፲ ጌታም መለሰ ።
ወይቤላ ሶበሰ ተአምሪ ጸጋሁ ለእግዚአብሔር ወመኑ ውእቱ ይስእለኪ ወይብለኪ አስትዩኒ ማየ ።
ውኅ አጠጭኝ ብሎ የለመነሽ ማንም እንደሆነ የእግዚአብሔርንስ ቸርነቱን ብታውቂ ። አንቲኒ ዓዲ እምስአልኪዮ ። አንችም በለመንሽው ነበር ። ወውእቱኒ እምወሀበኪ ማየ ሕይወት ። እርሱም የሕይወት ውኀን በሰጠሽ ነበር ። አንድም ውኅ አጠጭኝ ብዬ የምለምንሽ እኔ ኃይሉ ለአብ ወጸጋ ዘአሕዛብ ተብሎ የተነገረልኝስ እንደሆንኩ ብታውቂ አንችም በለመንሽኝ እኔም ማየ ሕይወትን በሰጠሁሽ ነበር ፤

፲፩ ወትቤሎ ይእቲ ብእሲት እግዚእየ ማኅየብኒ አልብከ ።

፲፩ ያችም ሴት ጌታዬ መቅጃ አልያዝኩም ለልማዱ ነጋድያን ውኅ በመንቀል ይይዛሉ። ከያዝከው ታጠጣኛለህ እንዳልል ውኅ በመንቀል አልያዝክ ፤
ወዓዘቅቱኒ ዕሙቅ ውእቱ ። በጅህ ታፍነህ ታጠጣኛለህ እንዳልልም ምንጩ ጥልቅ ነው እምአይቴ እንከ ለከ ማየ ሕይወት ።
የሕይወት ውኅ ከወዴት አለህ አለችው ።

፲፪ አንተኑ ተዐቢ እምያዕቆብ አቡነ ዘወሀበነ ዘንተ ዓዘቅተ ።

፲፪ የነቀፈብኝ መሰሏት በዚያውስ ላይ ይህን ምንጭ ከሰጠን ከያዕቆብ አንተ ትበልጣለህን ወውእቱኒ ሰትየ እምኔሃ ። እርሱ ከርሷ ጠጣ ፤

ወደቂቁኒ ።	ልጆቹም ።
ወአንስቲያሁኒ ።	ሚስቶቹም ።
ወእንስሳሁኒ ።	ከብቶቹም ።
ወጥሪቱኒ ።	ባሮቹም ።

ከርሷ ጠጡ ተወልዳለች ቢሉ የተመቸ አልተወለደችም ቢሉ በልማድ ። ስልምናሶር በሰማርያ አጀም ኮንታ የሚባል ጭፍራ ሠርቷል ። አንበሳ ተነሥቶ ይፈጃቸው ጀመር እንደምን ሁነዋል ብሎ ጠየቀ ኢያእመሩ ሕገ ለአምላክ ውእቱ ብሔር ። ሥርዓቱን አላወቁበትም ፤ በዚያ አገር ያዕቆብ አቡነ እግዚአብሔር አምላከነ የማይል እንጂ አይኖርበትም አንበሳ ተነሥቶ ይፈጃቸው ጀመር አሉት ምናሴ የሚባል ካህን በዴዋዌ ከርሱ ሄዶ ይኖራል አስተምራቸው ብሎ ሰዶት አሥተምሯቸው ያዕቆብ አቡነ እግዚአብሔር አምላከነ የሚሉ ሁነዋልና በልማድ ። አንድም ከርሱ ተወልዳለች። አንድም ምናሴ የሚባል ካህን በዴዋዌ ሂዶ ከሰንባላጥ ንጉሥ ምስር ተጋብቶ ይኖራል ፤ እሰና

ብተኝ አገሬ ልሂድ አለው ። ምን አሳጣሁህ ግድ ኑር አለው አይሆንም አለው ። ሂድ ብሎ አሰናበተው ። ቢሄድ ዘመዶቹ ከአሕዛብ ተጋብተህ ኑረሃል ብለው መልሰው አባረው ሰደዱት ተመልሶ ሄደ ። እኔማ ቀድሞስ አትሂድ ብየህ አልነበረም ወይም እንጂ እወዲ እዴየ ዲበ ደብረ ከርሜልም ያለው ይፈጸም ይሆናል ብሎ በምት ወደው በሀገርህ ቤተ መቅደስ ሠርተህ ካህን ሁነህ ኑር ብሎ ገንዘብ ሰጥቶ ሰዶታል ከዚህ ተወልዳለች ።

፲፫ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፲፫ ጌታም መለሰ ፡
ወይቤላ ኵሉ ዘይሰቲ እምዝ ማይ ይጸምዕ ዳግመ።
ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ሁለተኛ ይጠማል ።
ወዘሰ ይሰቲ እማይ ዘእሁቦ አነ ኢይጸምዕ ለዓለም።
እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ግን ለዘለዓለም አይጠማም ።

፲፬ አላ ውእቱ ማይ ዘእሁቦ አነ ይከውን ውስቴቱ ነቅዓ ማይ ዘይፈለፍል ለሕይወት ዘለዓለም ።

፲፬ እኔ የምሰጠው የዘላለም ሕይወት ውኃ ከርሱ ሲፈልቅ ሲፈስ ይኖራል እንጂ ። አንድም ወዘሰ ይሰቲ ብለህ መልስ እኔ ያስተማርኩትን ትምህርት እኔ የሰጠሁትን ልጅነት በተቀበለ ጽምዓ ነፍስ የለበትም ።
አላ ውእቱ ማይ ።
እኔ የማስተምረው ትምህርት በርሱ ቃል ሲነገር እኔ የሰጠሁት ልጅነት በርሱ ምክንያት ሲሰጥ ይኖራል እንጂ ።

፲፭ ወትቤሎ ይእቲ ብእሲት እግዚእየ ሀበኒዮ እምውእቱ ማይ

፲፭ ያችም ሴት ጌታዬ ከዚያ ውኃ ስጠኝ ።
ሀበኒ ኪያሁ እርሱን ስጠኝ ።
ከመ ኢይጽማዕ ።
እንዳልጠማ ።
ወኢይምጻእ ዝየ ዳግመ እቅዳሕ ማየ ።
ዳግመኛ ውኃ ልቀዳ እንዳልመጣ አንድም ኢይጸምዕ ዳግመ ብሎ ነበርና ሁለተኛ እንዳልጠማ ።

፲፮ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ሑሪ ጸውዒ ምተኪ ወንዒ ዝየ ።

፲፮ ጌታም ሄደሽ ባልሽን ጠርተሽ ይዘሽው ነይ አላት ።

፲፯ ወአውሥአቶ ይእቲ ብእሲት ።
፲፯ ያችም ሴት መለሰች ።
ወትቤሎ አልብየ ምት ።
ባልም የለኝ አለችው ።

፲፰ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ሠናየ ትቤሊ አልብየ ምት ።

፲፰ ጌታም አላት ባልም የለኝ ማለትሽ እውነትሽ ነው ።
ቀዲሙሰ ኃምስቱ አደው ነበሩ ምስሌኪ ።
አስቀድሞ አምስት ባሎች ነበሩሽ ።
ወይእዜሰ ዘሀሎ ምስሌኪ ኢኮነ ምተኪ ።
ዛሬ ግን ካንች ጋራ ያለው ባልሽ አይደለም በሳራ ወለተ ራጉኤል አስማንድዮስ የሚባል ጋኔን በጭንዋ አድሮ ፯ቱን ባሎቹዋን እንደ ገደለባት ። ይህችንም አምስቱን ባሎቹዋን ገድሎባታል ስለዚህ ልብሰ ቀለብ እየሰጠች በጐረቤት ታኖረው ነበር አንድም ኃምስቱ አደው ብለህ መልስ ። አምስቱን መጻሕፍተ ሙሴ ተቀብለሻል ። ወይእዜሰ ዘሀሎ በኵር እኔን ግን በኵር አላደረግሽኝም ።

ወዘንተሰ አማነ ትቤሊ ።
አልተወለደችም ቢሉ አልብየ ምት ማለትሽ እውነትሽ ነው ያይወልድሽ ያዕቆብን ። ያዕቆብ አቡነ ማለትሽ ሐሰትሽ ነው እንጂ ። ተወልዳለች ቢሉ ያዕቆብ አቡነ ማለትሽ እውነትሽ ነው እግዚአ ያዕቆብ እኔን ከያዕቆብ ጋራ አነጻጽረሽ አንተኑ ተዓቢ እምያዕቆብ አቡነ ማለትሽ ሐሰትሽ ነው እንጂ ። አንድም ማኅየብኒ አልብከ ማለትሽ እውነትሽ ነው ። ማየ ሕይወት እኔን እምአይቴ እንከለከ ማየ ሕይወት ማለትሽ ሐሰትሽ ነው እንጂ ።

፲፱ ወትቤሎ ይእቲ ብእሲት እግዚእየ እሬእየከ ከመ ነቢይ አንተ ።

፲፱ ያችም ሴት ጌታዬ ዐዋቂ ትመስለኛለህ አለችው ።

፳ አበዊነሰ በዝንቱ ደብር ሰገዱ ዘዳ፡፲፪፡፭ ።
፳ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ይሰግዱ ነበር ተወልዳለች ቢሉ ሎዛን ቀራንዮን እያሳየች ፡ አልተወለደችም ቢሉ ማናቸውንም ተራራ እያሳየች ።

ወአንትሙሰ ትብሉ ከመ በኢየሩሳሌም መካን ውእቱ ኀበ ይሰግዱ ።

እናንተ የኋላ ልጆች ግን የሚሰግዱ በኢየሩሳሌም ብቻ እንደሆነ ትናገራላችሁ ።

፳፩ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ እመንኒ ብእሲቶ ከመ ትመጽእ ሰዓት ወይበጽሕ ጊዜሁ አመ ኢዝንቱ ደብር ወኢበኢየሩሳሌም ዘይሰግዱ ለአብ አላ በበዝንቱ መካን ይሰግዱ ።

፳፩ አንች ሆይ በዚህም ተራራ ሁኖ በኢየሩሳሌም ሁኖ ለአብ የሚሰግዱበት ጊዜ እንዲደርስ ዕወቂ ። አንድም አመ ኢበዝንቱ ደብር ወኢበኢየሩሳሌም በዚህም ተራራ ብቻ በኢየሩሳሌም ብቻ አመ ኢይሰግዱ ለአብ የማይሰግዱበት ጊዜ እንዲ

ደርስ ዕወቂ ፡ አላ በኵሉ ገጸ መካን ይላል ባራቱ ማዕዘን ነው እንጂ ።

፳፪ እንትሙሰ ትሰግዱ ለዘኢተአምሩ ። ፬ ነገ ፲፯፡፵፩ ።

፳፪ እናንተ በሥራ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ።
ወንሕነሰ ንሰግድ ለዘነአምር ።
እኛ ግን በሥራ ለምናውቀው እንሰግዳለን ።
እስመ መድኃኒት እምነ አይሁድ ውእቱ ።
ተስፋ በሀገረ ተስፋ አምላክ በሀገረአምላክ ነውና።
አንድም አንትሙሰ ትሰግዱ እናንተስ በአካል ሦስት በባሕርይ በህልውና አንድ ብላችሁ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ ። እኛ ግን በአካል ሦስት በባሕርይ በህልውና አንድ ብለን ለምናውቀው እንሰግዳለን። እስመ መድኃኒት እምነ ይሁዳ መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ ከነገደ ይሁዳ ተወልዷልና ።

፳፫ ወባሕቱ ትመጽእ ሰዓት ።
፳፫ ባሕቱ ዋዌ ነው ጊዜም ይደርሳልና ።

መይእዜ ይእቲ አመ እለ በርቱዕ በአማን ሰጋድያን ይሰግዱ ለአብ በመንፈስ ወጽድቅ ።
በውነት በሚገባ ለአብ የሚሰግዱ በመንፈስና በጽድቅ ማለት በአብራክ ነፍስ ሁነው በንጽሐ ጠባይዕ ጸንተው ለአብ የሚሰግዱበት ጊዜም ዛሬ ነው። አንድም በመንፈስ ቅዱስ ልጆች ሁነው በጽድቀ አሚን ጸንተው ። አንድም በመንፈስ ቅዱስ በወልድ አምነው የሚሰግዱበት ጊዜ ዛሬ ነው ።
እስመ አብኒ ዘከመዝ የኃሥሥ እለ ይሰግዱ ሎቱ። አብ እንዲህ የሚሰግዱለትን ይወዳልና ።

፳፬ እስመ እግዚአብሔር መንፈስ ውእቱ ። ፪ ቆሮ ፫፥፲፯ ።

፳፬ እግዚአብሔር ረቂቅ ስለሆነ ።
ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ በመንፈስ ወበጽድቅ ሀለዎሙ ይስግዱ ሎቱ ።
የሚሰግዱለት በእብራክ ነፍስ ሁነው በንጽሐ ጠባይዕ ጸንተው ይሰግዱለት ዘንድ አላቸው ።

፳፭ ወትቤሎ ይእቲ ብእሲት አአምር ከመ ይመጽእ ማስያስ ዘይብልዎ ክርስቶስ ።

፳፭ ነግሯት ሳለ ያልነገራት መስሏት ለጠየቅሁህ መልስልኝ እንጂ ይኸንስ ክርስቶስ የሚባል ማስያስ እንዲመጣ አውቃለሁ ።
ወአመ መጽአ ውእቱ ይነግረነ ኵሎ።
በመጣም ጊዜ ሁሉን ያስተምረናል ። አንድም እንትሙሰ ትሰግዱ ለዘኢተአምሩ ። ብሏት ነበርና ምንዋ እናውቅ እናውቃለን እንጂ ክርስቶስ የሚባል ማስያስ እንዲመጣ ።
ወአመ መጽአ በመጣም ጊዜ እንዲነግረንእናውቃለን።

፳፮ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ አነ ውእቱ ዘእትናገረኪ ።

፳፮ ክርስቶስ የሚባል ማስያስ ይመጣል ። በመጣም ጊዜ ሁሉን ይነግረናል የምትዪው የምናገርሽ እኔ ነኝ አላት ። አንድም ክርስቶስ የሚባል ማስያስ ይመጣል የምትዪው እኔ ነኝ ። በመጣም ጊዜ ሁሉን ይነግረናል የምትዪው የምነግርሽ ነገር ነው ።

፳፯ ወእምዝ መጽኡ አርዳኢሁ ።

፳፯ ሖሩ ብሎ ነበርና ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ መጡ ።
ወአንከርዎ ። አደነቁት ።
እስመ ምስለ ብእሲት ይትናገር ።
ከሴት ጋራ ሲነጋገር አይተውታልና ብዙ ምሑራን መጻሕፍት ያላመኑበት ይህች ሴት ታምንብኛለች ብሎ ነው ብለው ። አንድም ለትሕትናው ሴት ወንድ ታናሽ ታላቅ አይለይለትም ብለው ።
ወባሕቱ አልቦ ዘይቤሎ ምንተ ተኃሥሥ ወምንተ ትትናገር ምስሌሃ ።
ነገር ግን ከርሷ ምን ትሻለህ ከርሷ ጋራ ምን ትነጋገራለህ ብሎ ደፍሮ የጠየቀው የለም ።

፳፰ ወኀደገት ቀሡታ ይእቲ ብእሲት ወሖረት ወአተወት ሀገረ ።

፳፰ ያችም ሴት ማድጋዋን ትታ ከከተማው ገባች ። ልብ ቀርቷት ፈጥና እንድትመለስ።

ወነገረት ለሰብእ ።
ለጐረቤቶችዋ ነገረች ለሰብእ ቤታ ይላል ለቤተ ሰዎቹዋ ነገረች ቤተ ሰብእ እያላት ውኃ ትቀዳለች ቢሉ በህገራቸው በሥራ መለያየት የለም ።

፳፱ ወትቤሎሙ ንዑ ትርአዩ ብእሴ ዘነገረኒ ኵሎ ዘገበርኩ ።

፳፱ የሠራሁትን ሥራ የነገረኝን ሰው ታዩ ዘንድ ኑ ።

፴ እንዳኢ ለእመሁ ክርስቶስ ።

፴ ክርስቶስም እንደሆነ እንጃ አለቻቸው ።

፴፩ ወወፅኡ እምሀገር ወሖሩ ኀቤሁ ።

፴፩ ከከተማው ወጥተው ወደሱ ሄዱ ።
፴፪ ወእምዝ ይቤልዎ አርዳኢሁ ረቢ ብላዕ እክለ።

፴፪ መጽኡ ብሎ ነበርና ። ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ መምህር ሆይ እህል ብላ አሉት ። ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አንሰ ብየ መብልዕ ዘእበልዕ ዘኢተአምርዎ እንትሙ ።

ጌታም አሳቸው የምበላው መብል አለኝ እናንተ የማታውቁት ።

፴፫ ወተብሀሉ አርዳኢሁ በበይናቲሆሙ ቦኑ እንጋ ሰብእ ዘአምጽአ ሎቱ መብልዓ ዘይበልዕ

፴፫ ደቀ መዛሙርቱም እርስ በርሳቸው እን ዳች የሚበላው ያመጣለት ሰው ይኖር ይሆን ተባባሉ። ወሚመ ዛቲ ብእሲት ።
ወይም ይህች ሴት አመጣልሃለሁ ብላው ይሆን ።

፴፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ሊተሰ መብልዕየ ውእቱ ከመ እግበር ፈቃዶ ለዘ ፈነወኒ ።

፴፬ የኔስ ምግቤ የላከኝ ያባቴን ፈቃድ አደ ርግ ዘንድ ነው ።
ወከመ እፈጽም ግብሮ ።
ሥራውንም እፈጽም ዘንድ

፴፭ አኮኑ አንትሙ እለ ትብሉ እስከ ራብዕ ወርኅ ይከውን ማዕረር ።

፴፭ እናንተ እስከ አራት ወር ። ድኅረ ራብዕ ወርኅ ይላል ካራት ወር በኋላ መከር ይደርሳል ትሉ የለምን ።

ወናሁ እብለክሙ አንሥኡ አዕይንቲክሙ ወነጽሩ ኀበ በሐውርት ከመ ፃዕድው ወበጽሐ ማዕረር ። እንዲህም የምትሉ እናንተ ዓይናችሁን አራምዳችሁ መከር እንደ ደረሰ አስተውሉ ።

እኔ ግን ዕለቱን ዘርቼ ዕለቱን አድርሼ አሳያችኋለሁ። እስከባለው በሀገራችን ሐምሌ ነሐሴ መስከረም ጥቅምት ድኅረ ባለው ከሰኔ አምስት ሐምሌ ነሐሴ መስከረም ፣ ድኅረ ጥቅምት ነው ፣ በሀገራቸው እስከ ባለው ጥር የካቲት መጋቢት ሚያዝያ ፣ ድኅረ ባለው ከታኅሣሥ አምስት ጥር የካቲት መጋቢት ፣ ድኅረ ሚያዝያ ነው እንድም እስካራተኛው ክፍለ ዘመን ሥጋዌ ይደረጋል ትሉ የለምን።አንደም ድኅረ ራብዕ ወርኅ ፣ ካራተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ሥጋዌ ይደ ረጋል ትሉ የለምን እንሥኡ አዕይንቲክሙ እን ዲህ የምትሉ ዓይነ ልቡናችሁን አራምዳችሁ ሥጋዌ እንደ ደረሰ ዕወቁ እኔ ግን ዕለቱን አስተምሬ ዕለቱን ከፍጹምነት አድርሼ አሳያችኋለሁ ። እስከ ባለው ዘመን አበው ዘመነ መሳፍንት ዘመነ ነገሥት ዘመነ ካህናት ድኅረ ባለው ዘመነ አበው ዘመነ መሳፍ ንት ዘመነ ነገሥት ድኅረ ዘመነ ሥጋዌ ነው ።

፴፮ እስመ ዘየአጽድኒ ይነሥኢ አስቦ ማቴ ፱፡፴፯ ሉቃ፡ ፲፪ ።

፴፮ የሚያጭድም ዋጋውን ያገኛል ወያስተ ጋብእ ፍሬ ለሕይወት ዘለዓለም ።

ለዘላለም ሕይወት ፍሬንም ይሰበስባል ። ወይ ምሥ ጢር ሂዶ ለሕይወት ዘለዓለም አለ ። አንድም እስመ ዘየአጽድኒ ። የሚያስተምር ሐዋርያ ዋጋ ውን ያገኛል ። ወያስተጋብእ ፍሬ የዘላለም ክብር ሲሆነው ፍሬ ክብርን ይሰበስባል ።

ከመ ኅቡረ ይትፌሥሑ ዘሂ ይዘርዕ ወዘሂ የአርር። የሚዘራም የሚያጭድም አንድ ሁነው ደስ ይላ ቸው ዘንድ

፴፯ ወዝንቱ ነገር ቃለ ጽድቅ እሙን ውእቱ ከመ ካልዕ ዘይዘርዕ ወካልዕ ዘየአርር ።

፴፯ የሚዘራ ሌላ የሚያጭድም ሌላ እንደ ሆነ ይህ ነገር በውነት የታመነ ነው አለ ። በሀገራቸው በሀገራችን ታሞ ሙቶ እገር ጥሎ ሂዶ በደንቢያ ግን የዘራውን አያጭደውም የርሱን ሲያሳጭድ አጊጦ ጥላ ይዞ ሲያሳጭድ ይውላል በነጋው ማጭዱን ይዞ ለሌላው ሲያጭድ ይሄዳል ። አንድም ከመ ኅቡረ ይትፌሥሑ ብለህ መልስ ይወርዳል ይወለዳል ብለው ትንቢት የተ ናገሩ ነቢያት ወረደ ተወለደ ብለው ያስተማሩ ሐዋርያት አንድ ሁነው ደስ ይላቸው ዘንድ ። ወዝንቱ ነገር፡ይወርዳል ብለው ትንቢት የተናገሩ ነቢ ያት ወረደ ተወለደ ብለው ያስተማሩ ሐዋርያት አንድ ሊንደሆኑ ይህ ነገር እውነት ነው ፡ ነቢያ ትን በክረምት ገበሬ ። ሐዋርያትን በበጋ ገበሬ መስሎ ይናገራል ። የክረምት ገበሬ ጧት ሲወጣ ምሳ ሳይበላ ይወጣል ቀን ከዋለበት ከውኃ ላይ ቆሞ ከላይ ውኃ ሲወርድበት ይውላል ማታም በተመለሰ ጊዜ ምግቡ ተዘጋጅቶ አይቀርብለትም ኀዘን ጠምቆ ያድራል ። የበጋ ገበሬ ጥዋት ሲወጣ ምሳውን በልቶ ይወጣል ከዋለበትም እሸቱን እንኩቶውን ሲበላ ይውላል ። ማታም በተመለሰ ጊዜ ምግቡ ተዘጋጅቶ ይቆየዋል እንጀራው በሌማት ጠላው በማቶት የክረምት ገበሬ ጧት ሲወጣ ምሳ ሳይበላ እንዲ ወጣ ነቢያትም ልጅነትን አላገኙም ከዋለበት ውኀ ላይ ቁሞ ውኀ ሲወርድበት እንዲውል ፣ መከራ ጸንቶባቸዋል ። በተመለሰም ጊዜም እራቱ ተዘጋጅቶ እንዳይቀርብለት ፣ ርድተ ገሃነም አልቀረ ላቸውም ፣ የበጋ ገበሬ ጧት ሲወጣ ምሳውንበልቶ እንዲወጣ ፡ ልጅነት አግኝተዋል ። ከዋለበት እሸት እንኩቶ ሲበላ እንዲውል ፡ ተአምራት ተድርገ ላቸዋል ። ማታ በተመለሰ ጊዜም እራቱ ተዘጋ ጅቶ እንዲቀርብለት ርደተ ገሃነም አላገኛቸውም።

፴፰ ወአንስ ፈነውኩክሙ ከመ ትእርሩ በዘ ኢጻመውክሙ ዘባዕድ ጻመወ ።

፴፰ እኔስ እናንተ ያልደከማችሁበትን ሌላ የደከመበትን ልትሰበስቡ ላክኋችሁ ።
አንትሙ ትባኡ ውስተ ጻማሆሙ ለኣልክቱ ።
እኒያ በደከሙበት እናንተ ትገቡ ዘንድ ። አንድም አንሰ ብለሀ መልስ እናንተ ይወርዳል ይወለዳል ብላችሁ ትንቢት ያልተናገራችሁለትን ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ብለው ትንቢት የተናገሩለትን ወረደ ተወለደ ብላችሁ ታስተምሩ ዘንድ ላክኋችሁ ። ነቢያት በመደመዱ ሐዋርያት ገደገዱ እንዲሉ ሁሉ ።

፴፱ ወብዙኃን እምይእቲ ሀገረ ሳምር እለ አምኑ ቦቱ በእንተ ዘትቤሎሙ ይእቲ ብእሲት ዘስምዓ ኮነት እንዘ ትብል ነገረኒ ኵሎ ዘገበርኩ ።

፴፱ የሠራሁትን ነገር ሁሉ ነገረኝ ብላ ያች ሴት ስለ ነገረቻቸው ከሰማርያ ሰዎች ያመኑበት ብዙ ናቸው ።

፵ ወበጺሖሙ ኀቤሁ ኵሎሙ ሳምራውያን አስተብቍዕዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ከመ ይንበር ኀቤሆሙ ።

፵ ሳምራውያን ሁሉ ወደርሱ መጥተው ሰንብትልን ብለው ጌታን ማለዱት ።

፵፩ ወነበሩ ህየ ሰኑየ መዋዕለ ።

፵፩ ከዚያም ሁለት ቀን ተቀመጠ መላልሳችሁ አስተምሩ ለማለት አብነት ለመሆን ።
ወብዙኃን ጥቀ እምኔሆሙ እለ አምኑ ቦቱ በእንተ ቃሉ ።
ይልቁንም ከቃሉ ሰምተው ያመኑበት ብዙ ናቸው ።

፵፪ ወይቤልዋ ለዛቲ ብእሲት አኮ እንከ በነገረ ዚአኪ ዘአመነ ቦቱ ።

፵፪ ያችንም ሴት ያመንበት አንቺ በነገርሽን አይደለም እሷት የሴት ደቀ መዛሙርት እንዳይሉን ብለው ውዳሴ ከንቱ ሽተው ። አንድም እውነታቸው ነው ክርሷ ከሰሙ የሰሙ ናቸው አንድም አንቺ በነገርሽን ብቻ አላመንበትም አንችስ እንዳኢሲአመ ውእቱ ክርስቶስ ብለሽ አጠራጥረሽን ነበር ።
አላ ለሊነ ጠየቅነ ወሰማዕነ ከመ ዝንቱ ውእቱ ክርስቶስ በአማን መድኅነ ዓለም ።
እኛ ከቃሉ ሰምተን በውነት የዓለሙ መድኃኒት ክርስቶስ እንደሆነ ዓውቀን አምንንበታል እንጂ ።

ዘከመ አሕየዎ ኢየሱስ በገሊላ ለወልደ ገብረ ንጉሥ ።

፵፫ ወእምድኅረ ሰኑይ መዋዕል ወፅአ እግዚእ ኢየሱስ እምህየ ወሖረ ካዕበ ገሊላ ።

፵፫ ከሁለት ቀን በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚያ ወጥቶ ሁለተኛ ወደገሊላ ሄደ ከተመችን ብላችሁ በአንድ ቦታ አትኑሩ ወጥታችሁ ወርዳችሁ አስተምሩ ለማለት አብነት ለመሆን ።

፵፬ ወለሊሁ እግዚእ ኢየሱስ ሰማዕተ ኮነ ከመ ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ። ማቴ፡፲፫፡፶፯ ማር፡ ፮፡፬ ሉቃ፡፬፡፳፬ ።

፵፬ እኮ እንከ በነገረ ዚአከ ዘአመነ ቦቱ ብለዋት ነበርና ካሀን በሀገሩ እንዳይከብር ጌታችን እሱ ራሱ መሰከረ።በዚያ ያልተያያዘ በሉቃስ የተያያዘ ።

፵፭ ወበዊአ ገሊላ ተቀበልዎ ኵሎሙ ገሊላውያን ። ማቴ፡፬፡፲፪ ማር፡ ፩፡፲፬ ሉቃ ፬፡፲፬ ዮሐ፡ ፪፡፱ ።

፵፭ ተራ ዋዌ አንድም ወበዊአ ገሊላ ተቀበልዎ ኵሎሙ ገሊላውያን ብሎ ነበርና ገሊላም በገባ ጊዜ የገሊላ ሰዎች ሁሉ አመኑበት ።
እለመ ርእዩ ኵሎሙ ተአምረ ዘገብረ በኢየሩሳሌም አመ በዓል ።
ለገቢረ በዓል ወጥቶ ሳለ በኢየሩሳሌም ያደረገውን ተአምራት ሁሉ አይተዋልና ።
እስመ እሙንቱሂ ሖሩ ለበዓል እርሳቸውም ለበዓል ወጥተው ነበርና ።

፵፮ ወሖረ ካዕበ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ገሊላ ኀበ ረሰየ ማየ ወይነ ።

፵፮ ጌታችንም ውኃውን ጠጅ ወዳደረገበት ወደ ቃና ሁለተኛ ሄደ ፡
ወሀሎ ህየ አሐዱ ገብረ ንጉሥ ሰብእ አብያታዊ ።
አብያታዊ ገንዘብ ያለው ገብረ ንጉሥ እለ ማዕዜመ እገብር ቤተ ለርእስየ ወያጠርያ አብያተ እምጽድቀ ዚአሆን እለ ትበልዑ አብያተ መበለታት እንዲል ።
አንድም ቤተሰብነት ያለው ባሪያ ቢወልድ ፍናጅን ፡ ፍናጅ ፡ ቅናጅን ፡ ቅናጅ አሰሰጥን ፡ አሰሰጥ አመለጥን ፡ አመለጥ ማን ቤቴን ማን ቤቴ ደረባ ብቴን ወይደዊ ወልዱ በቅፍርናሆም ሀሎ ይደዊ ። ልጁ በቅፍርናሆም ታሞ ነበር ።

፵፯ ወሰሚዖ ከመ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ እምይሁዳ ውስተ ገሊላ ሖረ ኀቤሁ ወሰአሎ ከመ ይረድ ወያሕዩ ሎቱ ወልዶ ።

፵፯ ጌታ ከይሁዳ ወደገሊላ እንደ መጣ ሰምቶ በሰማ ጊዜ ወርደህ ልጄን አድንልኝ ብሎ ለመነው ።
እስመ አልጸቀ ይሙት ።
ሊሞት ቀርቦ ነበርና ።
፵፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እመ ተአምረ ወመንክረ ኢርኢክሙ ኢተአምኑ ።

፵፰ ጌታም ተአምራት ካላያችሁ አታምኑም አላቸው ።

፵፱ ወይቤሎ ውእቱ ገብረ ንጉሥ ሰብአ አብያታዊ እግዚኦ ረድ ፍጡነ ዘእንበለ ይሙት ወልድየ ።

፵፱ ያም ገብረ ንጉሥ አቤቱ ልጄ ሳይሞት ፈጥነህ ወርደህ አድንልኝ አለው ድውይ መፈወስ እንጂ ሙት ማስነሣት የማይቻለው መስሎት ።

፶ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ሑር ወልድከሰ ሐይወ ።

፶ ጌታም አንተ አላመንከም እንጂ ልጅህስ ድኖልሃል ሂድ አለው ። አንድም እመ ተአምረ ወመንክረ ኢርኢክሙ ብለህ መልስ ። ተአምራት ካላያችሁ አታምኑምን አለው ፤ ማመኑንም አምናለሁ ይልቁንም ሳይሞት ፈጥነህ ወርደህ አድንልኝ አለው ወይቤሎ ወልድከሰ ሐይወ ። አንተ በጐ አምነኸ ልጅህም ድኖልሃል አለው ።
ወአምነ ውእቱ ብእሲ በቃል ዘይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ወሖረ ።
ያም ሰው ጌታ ወልድከሰ ሐይወ ባለው ቃል አምኖ ሄደ ።

፶፩ ወእንዘ ይወርድ ተቀበልዎ አግብርቲሁ ፤
፶፩ ሲሄድ ብላቴኖቹ ተገናኙት ።

ወዜነውዎ ወይቤልዎ ወልድከሰ ሐይወ አንተ በመከራ ሰንብተሃል እንጂ ልጅህስ ድኖዋል ። አንድም አንተም በጐ መጣህ ልጅህም ድኖልሃል ብለው ነገሩት ።
ወተስእሎሙ ሰዓታ እንተ ባቲ መጠነ ወይቤሎሙ ዓየ ጊዜ ሐይወ ።
የሰፈረውን ሰዓት ጠየቃቸው የዳነው ምን ጊዜ ነው አላቸው ።

፶፪ ወይቤልዎ ትማልም ጊዜ ሰብዓቱ ሰዓት ኀደጎ ፈጸንቱ ።

፶፪ እርሳቸውም ትናንት በሰባት ሰዓት ሆድ ዝማው ተወው አሉት አሕዛብ ጠንቃቆች ናቸውና ወልድከሰ ሐይወ ባለው ጊዜ ሰዓቱን ሰፍሮታል ።

፶፫ ወአእመረ አቡሁ ከመ ጊዜ ይእቲ ሰዓት እንተ ይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ወልድከሰ ሐይወ ።

፶፫ አባቱም ልጁ የዳነ ፤ ጌታ ልጅህስ ድኖልሃል ባለው ሰዓት እንደሆነ ዓወቀ ።
ወአምነ ቦቱ ውእቱ ።
እርሱም አመነ ።
ወኵሉ ሰብአ ቤቱ ።
የቤቱም ሰዎች ።

፶፬ ወዝንቱ ካዕበ ዳግሙ ለእግዚእ ኢየሱስ ዘገብረ ተአምረ መጺኦ እምይሁዳ ውስተ ገሊላ ።

፶፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መጥቶ ያደረገው ተአምራቱ ሁለተኛው ይህ ነው ፤ ለሐልዮው ፤ ለቦታው ወነውን በሐልዮ ጠጅ እንዳደረገው ፤ በሐልዮ አድኖ ነውና ወልድከሰ ሐይወ ፤ ያለው ። ለቦታው ምንም ድውዩ ያለው በቅፍርናሆም ቢሆን ወልድከሰ ሐይወ ያለው በገሊላ ሆኖ ነውና ።

በእንተ ምጥማቃት ዘጽሩጻጥቄ ።

ምዕራፍ ፭ ።

፩ ወእምድኅረዝ ኮነ በበዓሎሙ ለአይሁድ ዓርገ እግዚእ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ። ዘሌ. ፳፱ ፭ ዘዳ. ፲፯. ፩ ።

፩ ኮነ ያለውን ዓርገ ብሎ አመጣው ዝ ሲናገረው የመጣው ነው ፤ ከዚህ በኋላ አይሁድ በዓል በሚያከብሩበት ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ ። ተራ በዓል ነው ፤ አንድም ያልታወቀ በዓል አንድም ሠረቀ ወርኀ ። አንድም ሁለተኛ ፋሲካ ነው ። ያንስ ኋላ ያመጣዋል ብሎ በውስጥ በሚያመጣው ቀዳም ።

፪ ወቦ ውስተ ኢየሩሳሌም ምጥማቃት ዘጽሩጻጥቄ ቅልንብትራ ።

፪ በኢየሩሳሌም መጠመቂያ ነበር ዘጽሩጻጥቄ ዘፈውስ ዘበዓል ዘመሥዋዕት ዘጉባኤ ዘአባግዕ ቅልንብትራ ። ባንዱ ልሳን ቅልንብትራ የምትባል ፤ ወይቤልዋ ስማ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ ወይእቲ ቤተ ሣህል በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ ትባላለች ፤ ዘውእቱ ቤተ ሣህል ።
ቤተ ሳይዳም ማለት ቤተ ሣህል ማለት ነው ።
ወይእቲ ቀላየ አባግዕ ።
ቀላየ ዓባግዕ ዓጸደ አባግዕ ዓዘቅተ አባግዕ ምጥማቀ አባግዕ ምሕማሰ አባግዕ ይላል ንው ነሐምስ እንዲል ትግሬ ። ያችም የበጐች መጠመቂያ ናት ወባቲ ኃምስቱ ሕዋራት ።
አምስት እርከን አምስት መደብ አሳት እርከን እንደ ቍስቋም ፤ መደብ እንደ ማንኪት

፫ ወሀየ ይሰክቡ ብዙኃን ድውያን ።
፫ በእርከኑ በመደቡ ብዙ ድውያን ይተኛሉ ዕውራን ድውያን ያለውን ይተረትረዋል ።

ዕውራን ።	የታወሩ ።
ሐንካሳን ።	አንካሶች ።
ወይቡሳን ።	የሰለሉ ።
ወጽውሳን ፤	ልምሹ የሆኑ ።

ወጽቡሳን ፤
የተድበለበሉ ። ይተኛሉ ።
ወይጸንሑ ሁከተ ማይ ።
የውኀውን መናወጥ ይጠብቁ ነበሩ ።

፬ እስመ መልአከ እግዚአብሔር በጊዜ ይወርድ ውስተ ምጥማቃት ይትኀወክ ማይ ።

፬ መልአኩ በወረደ ጊዜ ውኀው ይነዋወጽ ነበርና ፤
ወዘይወርድ ቀዲሙ እምድኅረ ሁከተ ማይ ወይትሐጸብ የሐዩ እምዙሉ ደዌ ዘቦ ።
ወሀው ከተናወጠ በኋላ አስቀድሞ ወርዶ የተጠመቀ ካለበት ደዌ ሁሉ ይድን ነበር ። መልአኩ ስለምን ይወርዳል ቢሉ ለቀድሶተ ማያት ለአዕርጎተ መሥዋዕት ። ውኀውስ ስለምን ይናወጥ ነበር ቢሉ መልአኩ እንደ ወረደ ለማጠየቅ ለፈውስ ፤ ይህም ተራ ፀጎ ነው በክረምት የሚሞላ በበጋ የሚጐድል ። አንድም ፈለገ ቄድሮስ ነው ፤ አንድም ሰሎሞን በጥበብ ያገባው ወኀ ነው ። አንድም ወኀበ አውፅኡ ማየ ማእከለ ከልኤቱ ዓረፍት እንዲል ። ሕዝቅያስና ኢሳይያስ ከስድስተኛው ቆመ ብእሲ ያወጡት ወኀ ነው ቀዳም ቀዳም አንዳንድ ድውይ ይፈወሳል አይቀርም ፤ አይደግምም ፤ አለመቅረቱ ተእምራት ባባቶቻችን ጊዜ ይደረጋል እንጂ በኛ ዘመንስ ቀርቷል እንዳይሉ ። አለመደገሙ በአራት ፍጹም ድኅነት እንዳልተደረገ ለማጠየቅ እስመ አራት መንፈቀ ፍጹሜ ወኀዳጥ መከፈልት እንዲል ። መልአኩ የቀሳውስት ወኀ የጥምቀት ፭ ዕርከን ያ፭ አዕማደ ምሥጢር ። ፭ ድውያን ያ፭ቱ ጾታ ምእመናን ምሳሌ ፭ቱ ጾታ ምእመናን አዕሩግ ወራዙት እንስት ካህናት መነኰሳት። የአዕሩግ ጠራቸው ፍቅረ ንዋይ ነው ማን ይረዳናል ማን ያጸባናል እያሉ ገንዘብ ይሰበስባሉ ። ይህን ትቶ በወራዙት ጦር በዝሙት ይቃወማቸዋል በጥምቀት ባገኙት ኀይል ድል ይነሱታል የወራዙት ጦር ዝሙት ነው ይህን ትቶ በፍቅረ ንዋይ ይዋጋቸዋል በጥምቀት ባገኙት ኀይል ድል ይነሡባታል ። የአንስት ጦራቸው ትውዝፍት ነው የምንዝር ጌጥ ። ይህን ትቶ በሌላ ጦር ይዋጋቸዋል በጥምቀት ባገኙት ኀይል ድል ይነሡታልና ። የካህናት ጦራቸው ትዕቢት ነው እኢ ምሯችን ረቂቅ መዓርጋችን ምጡቅ እያሉ ይታበያሉ ይህን ትቶ በሌላ ጦር ይቃወማቸዋል በጥምቀት ባገኙት ኀይል ድል ይነሡታል። የመነኰሳት ጦራቸው ስስት ነው በሹት ጊዜ አያገኙትምና ይህን ትቶ በአንስሐስሖ ዘበከንቱ ይቃወማቸዋል በጥምቀት ባገኙት ኃይል ድል ይነሡታልና ።

፭ ወሀሎ ህየ ፩ ብእሲ ዘሠላሳ ወሰመንቱ ክረምቱ እምዘ ደወየ ።

፭ ከታመመ ሠላሳ ስምንት ዓመት የሆነው ድውይ ከዚያ አለ ።

፮ ወኪያሁ ርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ይሰክብ ውስተ ዓራቱ ።

፮ ጌታ እርሱ በደዌ ዳኛ ባልጋቁራኛ እንደ ተያዘ ዐውቆ ። እእመረ ከመ ጕንደየ ውስተ ደዌሁ ።
ይህ ሰው ደዌ ጠንቶበታል ።
በዚህ ሰው ደዌ ዘግይቶበታል አለ ።
ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ትፈቅድኑ ትሕየው ።
ልትድን ትወዳለህን አለው ።

፯ ወአውሥአ ውእቱ ድውይ ።
፯ ያም ድውይ መለሰ ።
ወይቤሎ እወ እግዚእ ።
አወን አቤቱ አለው ። እወ እንዲለው ያውቅ የለምን ቢሉ አለዋቂ የነበረ ሥጋን እንደ ተዋሐደ ለማጠየቀ ። እኮ ኢያእሚሮ ኀቡእተ እላ ከመ የሀብ መካን ለጥንተ ትስብዕቱ ዘኢየአምር ኅቡአተ እንዲል አንድም አወቅሁ ብሎ ሥራውን አይተውምና ። አንድም አስፈቅዶ ለማድረግ በዕለተ ዓርብ በጥፊ የሚመታው ነውና ያዳንህን ባሉት ጊዜ እርሱ የቀለብሳብ ነቱን አድኖኛል እንጂ አድነኝ ብየው አድኖኛልን እንዳይል ።
አላ ሰብእ አልብየ ከመ ሶበ ይትወሀክ ማይ ያውርደኒ ወይደየኒ ውስተ ምጥማቃት ። ውኀው በተናወጠ ጊዜ ከመጠመቂያው አውርዶ የሚጥለኝ ሰው የለኝም እንጂ አለው የሠላሳ ዓመት ጉልማሳ ቢየው ነጥቆ ይጥለኛል ብሎ ። አንድም አምስት ገበያ ሰው ይከተለው ነበርና እንዱን ያዝልኛል ብሎ ።
ወሶበ እመጽእ አነ ባዕድ ይቀድመኒ ወሪደ ።
እኔ በመጣሁ ጊዜ ሌላው ቀድሞኝ ወርዶ ይጠመቃል

፰ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ተንሥአ ንሣእ ዓራተከ ወሑር ።

፰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ተንሥተህ አልጋህን ተሸከመህ ሂድ አለው ። ሐተታ እንደ ማቴዎስ መምህር ኤስድሮስ ግን አልጋው ቅሉ የብረት አልጋ ነው ብለዋል ጽንዓ ተእምራቱን ለማጠየቅ ።

፱ ወሐይወ ሶቤሃ ውእቱ ብእሲ ወነሥአ ዓራቶ ወሖረ ።

፱ ያም ሰው ፈጥኖ ተነሥቶ አልጋውን ተሸከሞ ሄደ ።
ወሰንበት እሜሃ ውእቱ ዕለት መፃጉዕ የተፈወሰበት ቀኑ ቅዳሜ ነው ። አንድም እስመ ሰንበት እሜሃ ቅዳሜ ነበርና ።

ዘከመ አስተዋደይዎ አይሁድ ለኢየሱስ ።

፲ ወይቤልዎ አይሁድ ለውእቱ ብእሲ ዘሐይወ ሰንበት ውእቱ ዮም ። ዘፀ ፳ ፥ ፲፭ ኤር. ፲፯ ፳፩ ።

፲ ያን የዳነውን ሰው አይሁድ ዛሬ ቅዳሜ ነውና ወኢይከውነከ ትጹር ዓራተከ ። አልጋህን ተሸክመህ ልትሄድ አይገባህም አሉት ወኢታብኡ ጾረ ከቡደ ውስተ ኆዋሕዊሃ ለኢየሩሳሌም በዕለተ ሰንበት ። ያለውን የኤርምያስን ቃል ይዘው ትዝ ብሏቸው ብትል ።
ወአውሥአ ውእቱ ብእሲ ። እሱም መለሰ ።

፲፩ ወይቤሎሙ ዘአሕየወኒ ውእቱ ይቤለኒ ተንሥእ ንሣእ ዓራተከ ወሑር ።

፲፩ ያዳነኝ እሱ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለኝ አላቸው ።

፲፪ ወተስእልዎ አይሁድ ወይቤልዎ መኑ ውእቱ ብእሲሁ ዘይቤለከ ጹር ዓራተከ ወሑር ።

፲፪ ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ያለህ ማነው ብለው አይሁድ ጠየቁት ።

፲፫ ወውእቱሰ ዘሐይወ ኢያእመረ መኑ ውእቱ ዘአሕየዎ ።

፲፫ የዳነው እርሱ ግን ያዳነውን ማንም እንደ ሆነ አላወቀም ነበር ። እስመ ተሰወረ እግዚእ ኢየሱስ ማእከለ ብዙኃን ሰብእ እለ ሀለዉ በውእቱ መካን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ቦታ ባሉ በብዙ ሰዎች መካከል ተሰውሮ ነበርና ይህ ቅሉ ከሰንፍና አያወጣውም እንኳን ይህን ያህል ሥራ የሠራለትን ጥቂት ሥራ የሠራለትን ስንኳን ጠይቆ ማወቅ ይገባ ነበር ።

፲፬ ወእምዝ በሳኒታ ረከቦ ካዕበ እግዚእ ኢየሱስ ለውእቱ ዘሐይወ በምኵራብ ።

፲፬ ከዚህ በኋላ ጌታ ያን ያዳነውን ሰው በምኵራብ አገኘው ። ወይቤሎ ናሁኬ ሐየውከ ።
እነሆ ከደዌህ ድነሃል ።
ዑቅ ኢተአብስ ዳግመ እንከ ከመ ዘየአኪ ኢይርከብከ ።
እንግዲህ ከዚህ የጠና እንዳያገኝህ ሁለተኛ እንዳትበድል አስተውል አለው ። ከዚህ የጠና ምን አለ ቢሉ የቀድሞው ደዌ ሥጋ ነበር ። ዛሬ ግን ደዌ ነፍስ ነው ይህም አልቀረ በዕለተ ዓርብ ጌታን በጥፊ ቢመታው የመታበት እጁ ስሎ ደርቆ ቀርቷል ። ሐተታ ደዌ ዘንጽሕ ደዌ ዘዕሜት ደዌ ዘመቅሠፍት ደዌ ዘኃጢአት አለ ። ደዌ በንጽሕ እንደ ጢሞቴዎስ ። ደዌ ዘዕሜት እንደ ኢዮብ ደዌ ዘመቅሠፍት እንደ ሳኦል እንደሄሮድስ ደዌ ዘኃጢአት እንደዚህ ሰው ።

፲፭ ወሖረ ውእቱ ብእሲ ወነገሮሙ ለአይሁድ ከመ እግዚእ ኢየሱስ ውእቱ ዘአሕየዎ ።

፲፭ ያም ሰው ሄዶ ያዳነው ጌታ እንደሆነ ለአይሁድ ነገራቸው ።

፲፮ ወበእንተ ዝንቱ ያስተዋድይዎ አይሁድ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፲፮ ስለዚህም አይሁድ ጌታን ያጣሉት ያሳጡት ያካስሱት ነበር ወየኀሥሥዎ ይቅትልዎ ።
ሊገሉት ይፈልጉ ነበር ፤
እስመ ከመዝ ይገብር በሰንበት ።
ቅዳሜ ድውይ ይፈውስ ነበርና ።

፲፯ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፯ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ አቡየኒ እስከ ይእዜ ይገብር ፤
አባቴ እስካሁን ድረስ ሥራ ይሠራል አለ ፤ ሥነ ፍጥረትን ማመላለስ ነው ።
ወአነኒ ካዕበ ከማሁ እገብር ፤
እኔም እሠራለሁ ። ሥነ ፍጥረትን አመላልሳለሁ ፤ ይህስ ያልያዘው ነው ብሎ ፤ አባቴ ቅዳሜ ቅዳሜ አንዳንድ ድውይ ይፈውስ ነበር ። ወአነኒ ፤ እኔም ጉሕቈትን መፃጉዕን ፈወስኩ ።

፲፰ ወበእንተ ዝንቱ ፈድፋደ የኀሥሥዎ አይሁድ ይቅትልዎ ።

፲፰ ይልቁንም አቡየ ስላለባቸው አይሁድ ሊገድሉት ይሹ ነበር ። እስመ አኮ ከመ ሰንበተ ባሕቲቶ ዘይሥእር ፤
የሚሹት ሰንበትን ሻረ ብለው ብቻ አይደለም ።
ዳዕሙ ዓዲ አባሁ ይሬስዮ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሏል ወያዔሪ ርእሶ ምስለ እግዚአብሔር ። እግዚአብሔር ነኝ ብሏልና ስለዚህም ነው እንጂ ወእምዝ አውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
ከዚህ በኋላም ጌታ መለሰ ።

፲፱ ወይቤሎሙ አማን እብለክሙ ኢይክል ወልድ ገቢረ ዘእምኀቤሁ ወኢምንተኒ ።

፲፱ ወልድ ከራሱ ብቻ አንቅቶ ምንም ምን ሥራ አይሠራም ።
ዘእንበለ ዘርእዮ ለአብ ይገብር ከአብ በህልውና ያየውን በህልውና ያገኘውን ይሠራዋል እንጂ ። እስመ ግብረ ዘይገብር አብ ወልድኒ ኪያሁ ይገብር በአምሳሉ አብ የሚሠራውን ሥራ ወልድም ይሠራዋልና ።

፳ እስመ አብ ያፈቅር ወልዶ ወኵሎ ያሬእዮ ዘውእቱ ይገብር ።

፳ አብ ልጁን ይወደዋልና በህልውና የሚሠራውን ያሳየዋል ።
ወዘየዓቢ እምዝ ያሬእዮ ግብረ ያበላልጣል ። ድውይ ከመፈወስ ሙት ማንሣት እንዲበልጥ ከዚህም የበለጠ ሥራ ያሳየዋል ፥ ከ፡ አንትሙ ታእምሩ ወታንክሩ ።
እናንተ ታምኑ ዘንድ ወአንከረቶ ኵላ ምድር እንዲል

፳፩ ወበከመ አብ ያነሥኦሙ ለምውታን ወያሐይዎሙ ።

፳፩ አብ ሙታንን እንዲያሥነሣቸው እንዲያድናቸው ።
ከማሁ ወልድኒ ለዘፈቀደ ያሐዩ ወልድም ሊያድነው የወደደውን ያድነዋል ፈቀደ ለሁለቱም ነው ።

፳፪ እስመ አብሰ ኢይኴንን ወኢመነሂ ።
፳፪ አብ ታይቶ ማንንም ማንን አይገዛም ።
ታይቶ በማንም በማን አይፈርድም ።
አላ ኵሎ ኵነኔሁ አወፈዮ ለወልዱ ።
ታይቶ መግዛትን ታይቶ መፍረድን ለልጁ ሰጠው እንጂ ።

፳፫ ከመ ኵሉ ሰብእ ያከብርዎ ለወልድ በከመ ያከብርዎ ለአብ

፳፫ ሰው ሁሉ አብን ወላዲ ወልድን ተወላዲ ይለው ዘንድ ። ወዘሰ ኢያከብር ለወልድ ኢያከብር ለአብ ለዘፈነዎ ።

ወልድን የማያከብረው አብን አያከብረውም ማለት ወልድን ተወላዲ የማይለው ግን አብን ወላዲ አይለውም ። አባት አልባ ልጅ ። ልጅ አልባ አባት የለምና ።

፳፬ አማን አማን እብለክሙ ዘይሰምዕ ቃልየ ወየአምን በዘፈነወኒ ይረክብ ሕይወተ ዘለዓለም ።

፳፬ ያበላልጣል ። ሙት ከማንሣት ትንሣኤ ሕሊና እንዲበልጥ ። የኔን ቃል ሰምቶ አብ በላከኝ በኔ ። እኔን በላከኝ በአብ ያመነ የማታልፍ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳል ።
ወኢየሐውር ውስተ ደይን ።
ወደገሃነም አይሄድም ።
አላ አደወ እሞት ውስተ ሕይወት ።
ከሞት ወደሕይወት ይሄዳል እንጂ ።

፳፭ አማን አማን እብለከሙ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ ።

፳፭ ከትንሣኤ ሕሊና ትንሣኤ ልቡና እንዲበልጥ ፣ ጊዜው እንዲደርስ በውነት እነግራችኋለሁ ወይእዜ ውእቱ ከመ ምውታን ይሰምዕዎ ቃሎ ለወልደ እግዚአብሐር ።
ሙታነ ሕሊና የእግዚአብሐርን ልጅ ትምህርቱን የሚቀበሉበት ጊዜም ዛሬ ነው ።
ወእለሰ ይሰምዕዎ የሐይዉ ።
ትምህርቱን የሚቀበሉት ትንሣኤ ልቡና ይነሣሉ ።

፳፮ ወበከመ ለአብ ቦቱ ሕይወት ኀቤሁ ።
፳፮ ለአብ ሕይወትነት የባሕርዩ እንደሆነ ሕይወት እንዳለው ። ከማሁ ለወልድኒ ወሀቦ ሕይወተ ከመ ይኩን ሕይወት ኀቤሁ ሕይወት የባሕርዩ ይሆን ዘንድ ሕይወትን ሰጠው ።

፳፯ ወወሀቦ ሥልጣነ ከመ ይግበር ፍትሐ ወኰነኔ ።

፳፯ ይፈርድ ዘንድ ፣
እስመ ወልደ እግዚአብሐር ወልደ ዕጓለ እመ ሕያው የእግዚአብሐር ልጅ የሰው ልጅ ነውና ። ወሀቦ ሕይወተ ። ቦ ዘይቤላ መጻሕፍት በእንተ ትስብእቱ እንዲል ። አንድም የሰው ልጅ የእግዚአብሐር ልጅ ነውና ። ከመ ይግበር ፍትሐ ላለው ፣ ወቦ ዘይቤላ መጻሕፍት በእንተ መለኮቱ እንዲል አንድም ወልደ እግዚአብሐር ነውና ፣ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ነውና ወሀቦ ሕይወተ ከመ ይግበር ፍትሐ ። ቦ ዘይቤላ መጻሕፍት በእንተ ትስብእቱ ወበእንተ መለኮቱ ኀቡረ እንዲል ።

፳፰ ወበእንተ ዝንቱሰ ኢታንክሩ ።
፳፰ ይኸንንስ አታድንቁ ።

እስመ ትመጽእ ሰዓት ወይበጽሕ ጊዜሁ በዘይሰምዕዎ ቃሎ ለወልደ እግዚአብሐር ኵሎሙ እለ ውስተ መቃብር ።
ያበላልጣል ከትንሣኤ ልቡና ደገኛው ትንሣኤ ሥጋ እንዲበልጥ ። በመቃብር ያሉ ቃሉን የሚሰሙበት ጊዜ ይደርሳልና ።

፳፱ ወይወፅኡ እለ ሠናየ ገብሩ ውስተ ትንሣኤ ዘለሕይወት ። ማቴ፣ ፳፭፥ ፯ ።

፳፱ በጐ ሥራ የሠሩ ሁሉ በሕይወት በሚያኖር ትንሣኤ ይነሣሉ ።
ወእለሰ እኩየ ገብሩ ይትነሥኡ ውስተ ትንሣኤ ዘለደይን ። ክፉ ሥራ የሠሩ ግን በስቃይ ለመኖር በስቃይ በሚያኖር ትንሣኤ ይነሣሉ ።

፴ ኢይክል አንሰ ገቢረ ለልየ ዘእምኀቤየ ወኢምንትኒ ።

፴ እኔ ምንም ምን ከራሴ ብቻ አንቅቼ አላስተምርም ። አላ በከመ ሰማዕኩ እኴንን ። በሀልውና እንደሰማሁ የሰማሁትን አስተምራለሁ እንጂ ።
ወኵነኔየኒ ጽድቅ ውእቱ ።
ትምህርቴም እውነት ነው ።
እስመ ኢየኃሥሥ ፈቃደ ዚአየ ዘእንበለ ፈቃዱ ለዘፈነወኒ የላከኝ ያባቴን ፈቃድ ላደርግ እወዳለሁ እንጂ የኔ ፈቃድ ሊደረግ አልወድምና። አንድም የኔ ፈቃድ ካባቴ ፈቃድ ልዩ ሁኖ የኔ ፈቃድ ሊደረግ አልወድም የኔ ፈቃድ ካባቴ ፈቃድ ጋራ አንድ ነውና ያባቴ ፈቃድ ሊደረግ እወዳለሁ እንጂ ።

፴፩ ወእመሰ ለልየ ሰምዓ ኮንኩ ለርእስየ ኢኮነ ጽድቀ ስምዕየ ።

፴፩ እኔ ስራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ እውነት አይደለም የርሱ ሐሰት ሁኖ አይደለም ንጹሐን ነን በሚሉ ዘለፋ ሊሆንባቸው ነው እንጂ እርሱስ በሐልዮ እንዳልሠራ ለማጠየቅ ። ይመጽእ መልአኩ ለዝንቱ ዓለም ወኢይረክብ በላዕሌየ ወኢምንተኒ ብሂል በነቢብም እንዳልሠራ ለማጠየቅ ነቢይ ኢገብረ ኃጢአተ ፀ ኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ ብሎ መስክሮ ለታል በገቢርም እንዳልሠራ ለማጠየቅ ። መኑ ይዛለፈኒ በእንተ ኃጢአት ብሂል ። ንጹሐን ነን በሚሉ መፈራረጃ ሊሆንባቸው እንዲህ አለ እንጂ ።

፴፪ ወባሕቱ ካልዕ ውእቱ ሰማዕትየ ማቴ፡ ፫ ፲፯ ፣ ዮሐ· ፩ ፡ ፲፰ ።

፴፪ ምስክሬ ሌላ ነው አለ ። ዮሐንስ ፣ ፩ም ተእምራት ፡ መጻሕፍት አብ ወአእምር ከመ ጽድቅ ውእቱ ስምዑ ዘስምዓ ኮነ በእንቲአየ ስለኔም የመሰከረው ምስክሩ እውነት ነው ።

፴፫ አኮኑ አንትሙ ለአክሙ ኀበ ዮሐንስ ።
፴፫ እናንተ ወደ ዮሐንስ ልካችሁ አልነበረምን

ወነገረክሙ ስምዖ በጽድቅ በእንቲአየ ።
ስለኔ ምስክርነቱንስ በውነት ነግሯችሁ አልነበረምን።

፴፬ ወአንሰ አኮ ስምዓ ሰብእ ዘእፈቅድ ።
፴፬ ነገርግን እኔ የሰውን ምስክርነት አልሻም።

ወባሕቱ ዘንተ ዘእብል ከመ አንትሙ ትእመኑ ወትድኀኑ ። ነገር ግን ይኸን የምናገር እናንተ ታምኑ ትድኑ ዘንድ ነው እናንተ ታምኑ ትድኑ ዘንድ ይህን እናገራለሁ እንጂ ፣

፴፭ ወዝንቱ ውእቱ ማኅቶት ዘያሐቱ ወያበርህ
፴፭ የሚያበራ ፋና ይህ ነው ። ከዚያ ወሰሊሁስ ኢኮነ ብርሃን አለ ፣ ከዚህ እንዲህ አለ እንደምን ነው ቢሉ ፀሐይ በወጣ ጊዜ የፋናን ብርሃን የሚሻው እንደሌለ ጌታም ባስተማረ ጊዜ የዮሐንስን ትምህርት የሚሻው የለምና የዮሐንስንትምህርት በፋና የጌታን ትምህርት በፀሐይ መስሎ ተናገረ ። አንድም ፋና ለመጣለት ነው የሚያበራ ፀሐይ ግን ለሁሉ ነው ። እንደዚህም ሁሉ ዮሐንስ ያስተማረ ለመጣለት ነው ጌታ ያስተማረ ለሁሉ ነውና የዮሐንስን ትምህርት በፋና የጌታን ትምህርት በፀሐይ መስሎ ተናገረ ።

፴፮ ወአንትሙ ፈቀድክሙ ትትፌሥሑ፡ በብርሃኑ እሑተ ሰዓተ ።

፴፮ እናንተ በትምህርቱ መንፈቅ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ ።
ወአንሰ ብየ ሰማዕት ዘየዓቢ እምስምዓ ዮሐንስ ።
እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክርነት የሚበልጥ ምስክር አለኝ ።
እስመ ዝንቱ ግብር ዘወሀበኒ አቡየ እግበር ወእፈጽም ውእቱ ግብር ዘእገብር ሰማዕትየ ከመ አብ ፈነወኒ ።
በአብ ፈቃድ ሰው እንደሆንኩ ልሠራው ልፈጽመው አባቴ ገንዘብ ያደረገልኝ ተእምራት ምስክሬ ነው ።

፴፯ ወእቡየ ዘፈነወኒ ውእቱ ሰማዕትየ፡ ማቴ ፫፡ ፲፯ ዘዳ፡ ፬፡፲፪ ።

፴፯ የላከኝ አባቴም ምስክሬ ነው ።
ወእም አመ ኮንክሙ ቃሎ ኢሰማዕክሙ ።
ከሆነ ጀምሮ ማለት ወልድየ ዘበዙርየ ከተባላችሁ ጀምሮ ቃሉን በደብረ ሲና አልሰማችሁም ።
ወራእዮሂ ኢርኢክሙ ።
መልኩን አላያችሁም ።

፴፰ ወቃሉሂ አልብክሙ ወኢይነብር ኀቤክሙ
፴፰ ዓሠርቱ ቃላትን አልተቀበላችሁም ።አንድም ወእምአመ ኮንክሙ አያልክ መልስ ። ወልድየ ዘበዙርየ ከተባላችሁ ጀምሮ ቃሉን በደብረ ታቦር አልሰማችሁም ወራእዮሂ ። መልክአ መለኮቱን አላያችሁምን ። ወቃሉሂ ፣ ወንጌልን አልተቀበላችሁም ። አንድም ወልድየ ዘበዙርየ ከተባላችሁ ጀምሮ ወንጌልን አልተቀበላችሁም ። ወራእዮሂ ፣ መልክአ መለኮቱን አላያችሁም ወቃሉሂ ። አካላዊ ቃል አላደረባችሁም ። አንድም ስለሥጋዌ የተነገረውን ትንቢት አልተቀበላችሁም ።

እስመ ዘውእቱ ፈነወ ኪያሁ ኢአመንክሙ ።
እሱ በላከው አላመናችሁምና ።

፴፱ ኅሡ ትርአዩ ውስተ መጻሕፍት እንተ በቶን ይመስለክሙ ትረክቡ ሕይወተ ዘለዓለም ።

፴፱ በንባባቸው ብቻ የዘላለም ድኅነትን የምታገኙባቸው የሚመስሏችሁ መጻሕፍትን ሹ መርምሩ ። አንድም እስመ በቶን ።
በንባባቸው ብቻ የዘላለም ድኅነት የምታገኙባቸው ይመስላችኋልና ። አንድም የዘላለም ድኅነት የምታገኙበት ሃይማኖትን የምትረዱባቸውን አንድም የዘላለም ድኅነትን የምታገኙበት ሃይማኖትን ትረዱባቸዋላችሁና መጻሕፍትን ሹ መርምሩ ወእማንቱ ሰማዕትየ ። መጻሕፍት ምስክሮቼ ናቸው ።

፵ ወኢትፈቅዱ ትምጽኡ ኀቤየ ከመ ትርከቡ ሕይወተ ዘለዓለም ።

፵ ድኅነትን ታገኙ ዘንድ በኔ ልታምኑ አትሹም

፵፩ አንሰ ኢይፈቅድ ያድሉ ሊተ ሰብእ ።
፵፩ እኔ ግን የሌለኝን እምላክነት ሰው አምላክ ነህ ሊለኝ አልሻም ።

፵፪ ወባሕቱ አመርኩክሙ ከመ አልብክሙ ፍቀረ እግዚአብሔር ላዕሌክሙ ።

፵፪ ነገር ግን ፍቅረ እግዚአብሔር እንዳላደረባችሁ ነገርኳችሁ። አጠየቅክሙ ይላል አስረዳኋችሁ።

፵፫ አነ መጻእኩ በስመ አቡየ ወኢተወከፍክሙኒ ።

፵፫ እኔ ባባቴ ስም ፡ አባቴ ባወጣልኝ ስም ።
በስምዓ አቡየ ፡ አባቴ መሰከሮልኝ መጣሁ ።
ወኢተወክፍክሙኒ ።
አላመናችሁብኝም ።
ወእመ መጽአ ካልዕ በስመ ነፍሱ ኪያሁ ትትዌከፉ ሐሳዌ መሲሕ ግን ራሱ ባወጣው ስም ፤ እንድም ራሱ በመሰከረው ምስክር በመጣ ጊዜ ታምኑበታላችሁ ።

፵፬ እፎ ትክሉ አንትሙ አሚነ ዘተኃሥሡ ክብረ እምቢጽክሙ ወኢተኃሥሡ ክብረ እምኀበ እግዚአብሔር ባሕቲቱ ዋሕድ ፩ ቆሮ ፬፫ ።

፵፬ ክእግዚአብሔር ክብርን የማትሹ እንደና ናንተ ካለ ከዕሩቅ ብእሲ ክብርን የምትሹ እናንተ በኔ ማመን እንደምን ይቻላችኋል ። እፎ ትክሉ አንትሙ አሚነ ዘታበድሩ አድልዎ ሰቢጽክሙ እምታደልው ለዘባሕቲቱ እግዚአብሔር ዋሕድ ይላል ። ተዋርዳችሁ ተምራችሁ እግዚአብሔርን ብቻ አክብረን ብትሉት ይልቅ ለባልጀሮቻችሁ መስሎ መታየትን የምትወዱ እናንተ በኔ ማመን እንደምን ይቻላችኋል

፵፭ ኢይምስልክሙ ዘአነ አስተዋድየክሙ ኀበ አብ ።

፵፭ እኔ ወደ አብ የማጣላችሁ የማካስሳችሁ አይምሰላችሁ ። አላ ሀሎ ሙሴ ዘያስተዋድየክሙ ዘኪያሁ ትትዌከሉ ወትሴፈው ።
እናንተ ተስፋ የምታደርጉት የሚያጣላችሁ የሚያሳጣችሁ ሙሴ አለ እንጂ ።

፵፮ ሶበሰ አመንክምዎ ለሙሴ ኪያየኒ እምአመንክሙኒ ። ዘፍ ፫ ፲፭ ዘዳ. ፲፰ ፲፭ ።

፵፮ ሙሴንስ ተቀብላችሁት ቢሆን እኔንም በተቀበላችሁኝ ነበር ፣ እስመ በእንቲአየ ጸሐፈ ውእቱ ። እርሱ ስለኔ ጽፏልና ።

፵፯ ወእመሰ ዘጸሐፈ ሙሴ ኢተአምኑ እፎ ቃልየ ተአምኑ ።

፵፯ ሙሴ የጻፈውን ካልተቀበላችሁ ትምህርቴን እንደምን ትቀበሉኛላችሁ ።

ምዕራፍ ፮ ።

፩ ወእምድኅረ ዝንቱ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ ማዕዶተ ባሕረ ገሊላ ኀበ ጥብርያዶስ ። ማቴ ፲፬ ፲፫ ማር ፮ ፴ ሉቃ. ፱፡ ፲-፲ ።

፩ ዝ ሲናገረው የመጣ ነው ከዚህ በኋላ ጌታችን በገሊላ ባሕር ማዶ ወደጥብርያዶስ ሄደ እንድም የገሊላ ባሕር ማዶ ወደሚሆን ወደጥብርያዶስ ሄደ ።

፪ ወተለውዎ ብዙኃን አሕዛብ ።
፪ ብዙ ሰዎች ተከተሉት ።
እስመ ርእዩ ተአምረ ዘገብረ በላዕለ ድውያን ።
ድውይ ሲፈውስ አይተዋልና ።

፫ ወዓርገ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ደብር ወሀየ ነበረ ምስለ አርዳኢሁ ።

፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተራራ ላይ ወጥቶ ከዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ተቀመጠ ።

፬ ወቀርበ በዓለ ፋሲካሆሙ ለአይሁድ ።
፬ አይሁድ በዓል የሚያከብሩበት ቀን ደረሰ ።
፭ ወአንሥአ እግዚእ ኢየሱስ አዕይንቲሁ ወርእየ ብዙኃነ ሰብአ እንዘ ይመጽኡ ኀቤሁ ።

፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይኑን አራምዶ ብዙ ሰዎች ወደሱ ሲመጡ አየ ። ርእየን ቢያዩ ብዙኃን ሰብአ ይመጽኡን ቢያዩ ብዙኃን ሰብእ
ወይቤሎ ለፊልጶስ እምአይቴ ንሣየጥ ኅብስተ ዘናበልዖሙ ለእሉ ።
ፊልጶስን ለኔህ ሰዎች የምንመግባቸውን ኅብስት ከወዴት እንገዛለን ከየት እንግዛ አለው ።

፮ ወዘንተ ዘይቤ እንዘ ያሜክሮ
፮ እንዲህ ያለው ሊፈትነው ነው ወዘንተ ይቤ ሊፈትነው እንዲህ አለው ። የሚያመጣውን ቢናገር ሕጸጹን ለመግለጥ ። አንተ ኅብስት አበርክተህ ትመግባቸው የለምን ቢለው ብፅዓን ለመስጠት ነው ።
ወውእቱሰ የአምር ዘሀለዎ ይግበር ።
እርሱ ግን ሊያደርገው ዘንድ ያለውን ያውቅ ነበር ማለት ። ኅብስት አበርክቶ እንዲመግባቸው ።

፯ ወአውሥአ ፊልጶስ ።
፯ ፊልጶስም መለሰ ።
ዘክልኤ ምእት ዲናር ኅብስት ኢየአክሎሙ ከመ ይንሥኡ በበሕቅ ለለ ፩ እምኔሆሙ ፣
በሁለት መቶ ወቄት በሁለት ድሪም የተገዛ ኅብስት ክርሳቸው ወገን ጥቂት ጥቂት ማለት አንዳንድ ጉርሻ አይደርሳቸውም አለው ።

፰ ወይቤሎ አሐዱ እምአርዳኢሁ ዘውእቱ እንድርያስ እኁሁ ለስምዖን ጴጥሮስ ሀሎ ዝየ ወልድ ዘቦቱ ኃምስ ኅብስተ ስገም ወክልኤቲ ዓሣት ።

፰ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንድርያስ አምቡት ፪ገብስ እንጀራ ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና ከዚህ አለ አለው ። ሁሉም ሕጸጻቸውን ለመግለጥ ነው ።

፱ ወባሕቱ ምንተ ይበቍዓ እማንቱ ለዘመጠነዝ ሰብእ ።

፱ ነገር ግን እሊሀ ለዚህን ያህል ሰው ምን ይበቃሉ ።

፲ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ግበሩ ምርፋቃተ ለሰብእ ።

፲ ጌታም ይህስ ካለ መቀመጫውን አስናዱ አላቸው ።
ወብዙኅ ማዕሩ ለውእቱ መካን መስኩ በዚያ ሥፍራ እጅግ ምቹ ነበረ ። ግበሩ ያለው ምኑን ነው ቢሉ ዕን ጨቱን ድንጊያውን አንሱላቸው ሲል ።
ወረፈቁ ዲበ ማዕር አደዊሆሙ። ወንዶችም ከመስኩ ተቀመጡ ወየአክሉ ፶፻ ብእሲ ።
አምስት ሺህ ሰው ያህል ናቸው ።

፲፩ ወነሥአ እግዚእ ኢየሱስ ውእተ ኅብስተ ።
፲፩ ጌታም እንጀሮችን አንሥቶ ያዘ ።
ወአዕኰተ ።
አመሰገነ ።
ባረከ ወፈተተ ። ገመሰ ቈረሰ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ስጡ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው ።
ወአርዳኢሁኒ አቅረቡ ለሰብእ እለ ይረፍቁ ።
ደቀመዛሙርቶቹም ለተቀመጡት ሰዎች አቀረቡ ።
ወእምዓሣሁኒ ከማሁ መጠነ ፈቀዱ ።
ከዓሣውም የሚሹትን ያህል ሰጧቸው ፡

፲፪ ወእምድኅረ በልዑ ወጸግቡ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ አስተጋብኡ ዘተርፈ ፍተታተ ከመ ኢይትገደፍ ወኢምንተኒ እምኔሆን ።

፲፪ በልተው ከጠገቡ በኋላ ደቀመዛሙርቱን አንሡ ከርሳቸው ምንም ምን እንዳይቀር አላቸው ።

፲፫ ወአስተጋብኡ ። ሰበሰቡ ።
፲፫ ወመልአ ዓሠርተ ወክልኤተ መሳይምተ እምኃምስቱ ኅብስተ ሰገም ዘተርፈ እምዘ በልዑ ወጸግቡ ።
በልተው ከጠገቡ በኋላ ከተረፈው ከቀረው የተረፈው የቀረው ቁርስራሽ ዐሥራ ሁለት መሶብ ዐሥራ ሁለት ቅርጫት መላ ። ወትትሐነጺ ምዝነሠቱኪ ወእምዘረወዩ አግማሊሁ ነሥአ ኢያውብር አዕኑገ ዘወርቅ እንዲል ። የበረከተ ኅብስት መገናኛ እንደ ምን ነው ቢሉ እንደ ዮሐንስ ። ወአንሥአ እግዚእ ኢየሱስ አዕይንቲሁ ወርእየ ብዙኃነ ሰብአ እንዘ ይመጽኡ ኀቤሁ ወይቤሎ ለፊልጶስ እምአይቴ ንሣየጥ ኅብስተ ዘናበልዖሙ ለእሉ አላቸው ፡ ወምሴተ ከዊኖ እንደ ማቴዎስ ። ወእምድኅረ ብዙኅ ሰዓት እንደ ማርቆስ ፡ ወተቈልቈለ ፀሐይ እንደ ሉቃስ ፤ መገናኛ ዮሐንስ ፡ በተገናኝ ፡ ሲመሽ ማለት ነው ። ፈንዎሙ ማቴዎስ ፡ ሠዓር ሰብአ ማርቆስ ፡ ፍትሖሙ ሉቃስ ፡ መገናኛው ዮሐንስ በተገናኝ አሰናብት አሉት አሰናብት ቢሉት እንደ ፲ቱ አኮ መፍትው ይሑሩ ርኁባኒሆሙ አላ ሀብዎሙ አንትሙ ዘይበልዑ አላቸው እንደ ማርቆስ ፡ ንሑርኑ ንሣየጥ በ፪፻ ዲናር ኅብስተ ዘናበልዖሙ ለእሉ ይሉታል ። እንደ ዮሐንስ ፡ ዘ፪፻ ዲናር ኅብስት ኢያአክሎሙ ከመ ይንሥኡ በበሕቅ ለለ ፩ዱ እምኔሆሙ አሉት ፡ እንደ ማርቆስ ፡ ሑሩ ወርእዩ ሚመጠን ኅባውዝ ብክሙ ይላቸዋል ። እንደ ሦስቱ አልብነ ዝየ ዘእንበለ ኃምስ ኅብስት ወክልኤቲ ዓሣት እንደ ዮሐንስ ፡ ሀሎ ዝየ ወልድ ዘቦ ኃምስ ኅብስት ሰገም ወክልኤቲ ዓሣት ፡ እንደ ሉቃስ ፡ ለእመ ኢሖርነ ንሣየጥ ይሉታል ። ይህንስ ትታችሁ ግበሩ ምርፋቃተ ይላቸዋል ፡ ይኸንስ ለምን ይሻዋል ቢሉ ከወንድሞቹ ለማያያዝ ሰማያዊ ኅብስትን የሚያመጣ ነውና ከርሱ ለማነጻጸር ።

፲፬ ወርእዮሙ ሕዝብ ዘገብረ ተአምረ እግዚእ ኢየሱስ ይቤሉ አማን ነቢይ ውእቱ ዝንቱ ዘመጽአ ውስተ ዓለም ።

፲፬ ሕዝቡ ጌታ ያደረገውን ተአምራት አይተው ነቢየ ያነሥእ ተብሎ የተነገረለት በውነት ወደዚህ ዓለም የመጣው የአብ የባሕርይ ልጅ ነው አሉ ።

ዘከመ ሖረ ኢየሱስ ዲበ ማይ

፲፭ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ይመጽኡ ይምስጥዎ ወያንግሥዎ ተግኅሠ ውስተ ደብር ባሕቲቶ ።

፲፭ ቢራቡ ያመስል ። ቢታመሙ ይፈውሳል ። ቢሞቱ ያሥነሣል እንዲህ ያለውን ቢያነግሡት ምን ይብሳል ብለው ይዘው ሊያነግሡት እንደወደዱ አውቆባቸው ለብቻው ወደ ተራራ ሄደ እንሹማችሁ ባሏችሁ ጊዜ ሽሹ አትገኙ ለማለት አብነት ለመሆን መውጣቱ ግን ሰው የማያነግሠኝ ልዑለ ባሕርይ ነኝ ሲል ።

፲፮ ወመስዮ ወረዱ አርዳኢሁ ውስተ ባሕር ።
፲፮ ሲመሽ በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር ወረዱ ።

፲፯ ወዐርጉ ሐመረ ወሖሩ ማዕዶተ ባሕር ኀበ ቅፍርናሆም ።
፲፯ በመርከብም ሁነው በባሕር ማዶ ወደቅፍርናሆም ሄዱ ።
ወናሁ ኮነ ጽልመት ወድአ ።
ፈጽሞ ጨልሞ ነበር ።
ወዓዲሁ ኢመጽአ እግዚእ ኢየሱስ ኀቤሆሙ ።
ጌታ ግን ገና አልመጣም ነበር ።

፲፰ ወባሕርሰ ይትሀወክ ።
፲፰ ባሕሩም ይነዋወጥ ነበር ።
እስመ ዓቢይ ነፋስ ይነፍሕ ውስቴቱ ።
ጽኑ ነፋስ ተነሥቷልና ይነፍሳልና ።
፲፱ ወኀሊፎሙ መጠነ ፳ወ፭ቱ ምዕራብ ።
፲፱ ሀያ አምስት ምዕራፍ ከሄዱ በኋላ ።

አው ሠላሳ ።
ወይም ፴ ምዕራፍ ከሄዱ በኋላ ፤
ርእይዎ ለእግዚእ ኢየሱስ እንዘ የሐውር ዲበ ባሕር ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በባሕር ላይ ሲሄድ አዩት ማጠራጠሩ ስለምን ነው ቢሉ የባሕር ነገር በዓይነ ገመድ ነው እንጂ ለሥፍር አይመችምና ግብርም እንዳይገባለት ነገሩ ተራ ቢሆንበት ። አንድም በዓቢይ ፳፭ በንኡስ ፴ ምዕራፍ።ወሶበ ቀርበ ኀበ ሐመሮሙ። ወደ መርከቡ በቀረበ ጊዜ ።
ወፈርሁ ወደንገፁ ፈሩ ።

፳ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አነ ውእቱ ወኢ ትፍርሁ ።

፳ ጌታምእኔ ነኝ አይዟችሁ አትፍሩአላቸው ።
፳፩ ወእንዘ ይፈቅዱ ያዕርግዎ ውስተ ሐመር በጽሐት ሐመር ሶቤሃ ውስተ ምድር ኀበ ፈቀዱ ይሑሩ ።

፳፩ ወደመርከብ እናወጣዋለን ሲሉ መርከቢቱ ሊሄዱባት ወደ ወደዱባት ወደብ ደረሰች ፣ ማቴዎስ ወዓረገ አለ ፣ ከዚህ እንዲህ አለ ። እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ፣ ነገር እንደ ማቴዎስ ነው ። ምድር ቤትና ደርብ ነው ከምድር ቤቱ ወጥቷል ከደርቡ አልወጣምና ዮሐንስ አልወጣም አለ አንድም ነገር እንደ ዮሐንስ ነው ። አልወጣም ማቴዎስ ወዐረገ ማለቱ ነፋሱ ማዕበሉን በመርከቡ ልክ ያወጣው ነበር ጌታም ማዕበሉን እየተረገጠ በመርከቡ ልክ ይታይ ነበርና ።

፳፪ ወበሳኒታ ሰብእ ብዙኀ እለ ይቀውሙ ማዕዶተ ባሕር ርእዮሙ ከመ አልቦ ህየ ካልዕ ሐመር ዘእንበለ አሐቲ ሐመር ።

፳፪ ሳኒታን አቆየው ። ሁለት መርከብ ነበር ባንዱ ሐዋርያት ሄደውበታል ። ከባሕሩ ማዶ ያሉ ሰዎች ካንዲት መርከብ በቀር ሌላ መርከብ እንደሌለ ባዩ ጊዜ ፤
ወከመሂ ኢዓርገ እግዚእ ኢየሱስ ምስለ አርዳኢሁ ውስተ ሐመር ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመርከብ ተጭኖ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ እንዳልሄደ ባዩ ጊዜ ።
አላ አርዳኢሁ ባሕቲቶሙ ሖሩ
ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ሄደዋል እንጂ ።

፳፫ ወመጽአ ካልዓትኒ አሕማር እምጥብርያዶስ ቅሩብ ብሔር ኀበ በልዑ ኅብስተ ዘባረከ እግዚእነ።

፳፫ ሌሎችም መርከቦች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስት አበርክቶ ካበላበት ቦታ አቅራቢያ ከሚሆን ከጥብርያዶስ መጡ ።

፳፬ ወሶበ ርእዩ እሙንቱ ሰብእ ከመ ኢሀሎ እግዚእ ኢየሱስ ህየ ።

፳፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከዚያም እንደሌለ ባዩ ጊዜ ።
ወኢአርዳኢሁ ።
ደቀ መዛሙርቱም እንደሌሉ ባዩ ጊዜ ።
ዓርጉ ውስተ ውእቶን አሕማር ።
በሳኒታ ዓርጉ ባለ ፤ በነጋው በቀረው መርከብ ከጥብርያዶስም በመጡት መርከቦች ተጭነው ።
ወሖሩ ወበጽሑ ቅፍርናሆም ይኅሥሥዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እየፈለጉት ሄዱ ። ቅፍርናሆም ደረሱ ። አንድም ወበሳኒታ ብለህ መልስ ። የሐሊና አስተያየት ነው ። አንድ መርከብ ነበር በርሱም ሐዋርያት ሄደውበታል ፣ አንድ መርከብ እንደ ነበረ ያውም እንደሌለ ባዩ ጊዜ ፤ ወከመሂ ኢዓርገ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ በመርከብ እንዳልሄደ ፤ አላ አርዳኢሁ ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሄደዋል እንጂ ወመጽአ ካልዓትኒ አሕማር ፤ እምጥብርያዶስ ሌሎች መርከቦችም ከጥብርያዶስ መጡ ።
ወሶበ ርእዩ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከዚያ እንደሌለ ወኢአርዳኢሁ ፤ ደቀ መዛሙርቱም እንደሌሉ ባዩ ጊዜ ዓርጉ ውስተ ውእቶን አሕማር ። ከጥብርያዶስ በመጡት መርከቦች ተጭነው ጌታችንን እየፈለጉት ቅፍርናሆም ደረሱ ።

፳፭ ወሶበ ረከብዎ በማዕዶተ ባሕር ይቤልዎ ረቢ ማእዜ መጻእከ ወበጻሕከ ዝየ ።

፳፭ ባሕሩን ተሻግሮ ባዩት ጊዜ መምህር ሆይ ከዚህ ምን ጊዜ መጣህ ምን ጊዜ ደረስህ አሉት ።

፳፮ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፳፮ ጌታም መለሰ ።

ወይቤሎሙ አማን አማን እብለክሙ ከመ አኮ አንትሙ ዘተኃሥሡኒ በእንተ ዘርኢክሙ ተአምራት ።
እናንተ የምትሹኝ ተአምራት ስላያችሁ እንዳይደለ በውነት እነግራችኋለሁ ።
አላ በእንተ ዘበላዕክሙ ኅብስተ ወጸገብክሙ ።
ኅብስት አበርክቼ ስለአበላኋችሁ ነው እንጂ ።

፳፯ ተገበሩ እንከሰ ። ማቴ፡፫ ፣ ፲፰ ዮሐ ፩ ፣ ፴፪
፳፯ ከእንግዲህስ ወዲህ ጻሩ ።
አኮ ለመብልዕ ኃላፊ ።
መጣራችሁም ለኃላፊው መብል አይደለም ።

አላ ለመብልዕ ዘይነብር ለሕይወት ዘለዓለም ዘይሁበክሙ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
የዘላለም ሕይወት ሊሆን የሰው ልጅ ክርስቶስ ለሚሰጣችሁ ለማያልፈው ምግብ ነው እንጂ ።
እስመ ለዝሰ እግዚአብሔር ሐተሞ ።
ይኸነን ሥጋዊውን ምግብ እግዚአብሔር አብ አሳልፎታልና ።
አኮ ለመብልዕ ኃላፊ ፤ ወገጸ ከዋክብት የሐትም እንዲል አንድም ሥጋን ራሱን አስመስሎታልና ።
አላ ለመብልዕ ዘይነብር ለሕይወት ዘለዓለም በከመ የሐትሙ እለ የሐትሙ መዓረ ግራ በማኅተመ ወርቅ እንዲል ።
የኔን አምላክነት ሰውሮታል እኮን የኔን አምላክነትስ ሰወረው ኅትም ወኢትጽሐፍ እንዲል ።

፳፰ ወይቤልዎ ምንተ ንሬሲ ከመ ንግበር ግብረ እግዚአብሔር ፤

፳፰ እግዚአብሔር የሚወደውን ሥራ እንሠራ ዘንድ ምን እናድርግ ንሬሲ ምን እናደርጋለን አሉት ።

፳፱ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ። ፩ ዮሐ፡፫፡ ፳፫
፳፱ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ዝንቱ ውእቱ ግብረ እግዚአብሔር ከመ ትእመኑ በዘፈነዎ ውእቱ ።
እግዚአብሔር የሚወደው ሥራ እርሱ በላከኝ በኔ እንድታምኑ መሆን ነው ።

፴ ወይቤልዎ ምንተ ተአምረ ትገብር ከመ ንርአይ ወንእመን ብከ በዘገበርከ ።

፴ የሠራኸውን ሥራ አይተን በሠራኸው ሥራ እናምንብህ ዘንድ ምን ሥራ ትሠራለህ አሉት ።

፴፩ አበዊነሰ መና በልዑ በገዳም ዘፀ፡፲፮ ፡ ፲፬ ዘኁ፡፲፩ ፡ ፯ መዝ፡፸፯ ፡ ፯-፳፭ ዮሐ፡ ፲፮ ፡ ፳ ።

፴፩ ኅብስት አበርክቼ መግቤያችሁ የለምን ትለን እንደሆን እንዲህ ያለስ ቀድሞ አባቶቻችን መናውን ተመግበዋል ።
በከመ ጽሑፍ ኅብስተ እምሰማይ ወሀቦሙ ይብልዑ ።
ሰማይን አይሻውም ሊመገቡት መናውን ሰጣቸው ተብሎ ተጽፎ እንዳለ ፤

፴፪ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አማን አማን እብለክሙ አኮ ሙሴ ዘወሀበክሙ ውእተ ኅብስተ እምሰማይ ።
መናውን ሙሴ አልሰጣችሁም ።
አላ አቡየ ወሀበክሙ ኅብስተ ጽድቅ እምሰማይ ።

፴፪ ነገር ግን አባቴ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ ሰጣችሁ መናውንስ ኅብስተ ጽድቅ አይለውም ብሎ ኅብስተ ጽድቅ እኔን ሙሴ አልሰጣችሁም አባቴ ሰጣችሁ እንጂ ፤ አንድም ከመ እምላዕሉ አውረድከ ሥጋ ይለዋል በሊቁ ብሎ ከሰማይ ሥጋ ይዘህ እንደ መጣህ ምን ምልክት አለህ አሉት ፤
አበዊነሰ ፤ ኅብስት አበርክቼ መግቤያችሁ የለም ትለን እንደሆነ ይህስ ያለውን ማበርከት ነው የሌለውንስ አባቶቻችን መናውን ተመግበዋል ። በከመ ጽሑፍ ኅብስተ እምሰማይ ወሀቦሙ ይብልዑ ፤ ሊመገቡት ከሰማይ ሰጣቸው ተብሎ ተጽፎ እንዳለ ፤ ወይቤሎሙ አኮ ሙሴ ዘወሀበክሙ እምሰማይ ሙሴ መናውን ከሰማይ አልሰጣችሁም ያፍ በበረረ ዘንግ በተወረወረ ከሰማይ ወረደልን ይባላልን ፤ ልብስህ አላለቀ ጫማህ አልወለቀ በትርህ አልወደቀ እንዲሉ፤ ከውቅያኖስ በደመና አይበት ተቋጥሮ በነፋስ ወደ ልጋዝ ተጭኖ መልኩ በረድ መስሎ መጠኑ ድንብላል አህሎ ወእንዘ የኃድግ ሀቦ ይላል፤የውርጭ ገበታ እየተነጸፈ አርባ ዘመን እያዘነበላቸው እስራኤል መናውን ተመግበዋልና ፤ አንድም ኅብስተ ጽድቅ እኔን ሙሴ አልሰጣችሁም አባቴ ከሰማይ አውርዶ ሰጣችሁ እንጂ ።

፴፫ እስመ ኅብስቱ ለእግዚአብሔር ውእቱ ዘወረደ እምሰማይ ።

፴፫ የእግዚአብሔር ኅብስቱ ከሰማይ የወረደ ነውና ።
ወይሁብ ሕይወተ ዘለዓለም ።
የዘለዓለም ድኅነትንም ለሰው ይሰጣልና ።

፴፬ ወይቤልዎ እግዚኦ ሀበኒ በኵሉ ጊዜ እምውእቱ ኅብስት ።

፴፭ አቤቱ ዘወትር ከዚያ ኅብስት ስጠን አሉት።
፴፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ።

፴፭ ጌታም የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ አላቸው።
ዘመጽአ ኀቤየ ኢይርኅብ ።
ወደኔ የመጣ ማለት በኔ ያመነ አይራብም ።
ወዘሂ የአምን ብየ ኢይጸምዕ ለዝሉፉ ።
በኔ ያመነም ለዘላለም አይጸማም ። አንድም በኔ ያመነ ረኃበ ነፍስ ጽምዓ ነፍስ የለበትም ።

፴፮ ወእቤለክሙ ባሕቱ ርኢክሙኒ ወኢአመንክሙኒ ።

፴፮ ነገር ግን አይታችሁኝ አልተቀበላችሁኝም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፴፯ ወኵሉ ዘወሀበኒ አቡየ ይመጽእ ኀቤየ ።
፴፯ አባቴ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ የሰጠኝ ሁሉ በኔ ያምናል ።
ወለዘሂ መጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወፅኦ አፍአ ።
በኔ ያመነውንም ከመንግሥተ ሰማይ አፍአ ወደ

ገሃነም አላወጣውም ፤ ከቀደመው ሀገረ ምስካይ ሲለይ ከገባ በኋላ ኃጢአቱ ተመርምሮ ወጥቶ ይደበደባል ። መንግሥተ ሰማይ ግን ከገቡ መውጣት ካገኙ ማጣት የለምና ።

፴፰ እስመ ወረድኩ እምሰማይ አኮ ከመ እግበር ፈቃድየ ።

፴፰ ከሰማይ የወረድኩ የኔን ፈቃድ ላደርግ አይደለም ።
ዘእንበለ ፈቃዱ ለዘፈነወኒ ።
የላከኝ ያባቴን ፈቃድ ላደርግ ነው እንጂ ። አንድም የኔ ፈቃድ ካባቴ ፈቃድ ልዩ ሁኖ የኔን ፈቃድ ላደርግ ሰው አልሆንኩም አልወረድኩም የኔ ፈቃድ ካባቴ ፈቃድ ጋራ አንድ ነውና ያባቴን ፈቃድ ላደርግ ነው እንጂ ፤

፴፱ ወዝንቱ ውእቱ ፈቃዱ ለዘፈነወኒ አብ ።
፴፱ የላከኝ ያባቴም ፈቃድ ይህ ነው ።
ከመ ኵሉ ዘወሀበኒ ኢይትኀጐል እምኔሆሙ ወኢ አሐዱሂ ።
በኔ ካመኑ አንዱ ስንኳን እንዳይጐዳ መሆን ነው ።
አላ አነ አንሥኦ በደኃሪት ዕለት ።
በዕለተ ዓርብ አሥነሣዋለሁ ።

፵ ወዝንቱ ውእቱ ፈቃዱ ለዘፈነወኒ አብ ።
፵ የላከኝም ያባቴ ፈቃድ ይህ ነው ።
ከመ ኵሉ ዘርእዮ ለወልድ ወአምነ ቦቱ ይረክብ ሕይወተ ዘለዓለም ።
ወልድን አይቶ ያመነበት ሁሉ የዘላለም ድኅነትን ያገኝ ዘንድ ነው ።
ወአነ አነሥኦ በደኃሪት ዕለት ።
በዕለተ ትንሣኤ አድነዋለሁ ።

፵፩ ወአንጐርጐሩ አይሁድ በእንቲአሁ እስመ ይቤሎሙ አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማይ ።

፵፩ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ስላላቸው አይሁድ በርሱ ምክንያት ታወኩ ።
፵፪ ወይቤሉ አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ኢየሱስ ።

ወልደ ዮሴፍ ዘለሊነ ነአምር አባሁ ወእሞ ። ማቴ፣ ፲፫ ፣ ፶፭ ማር፣ ፮ ፣ ፫ ።

፵፪ እኛ አባት እናቱን የምናውቅ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን ።
ወእፎ እንከ ይእዜ ይብለነ እምሰማይ ወረድኩ ።
አወይ ውሸት አወይ ማታለል እንደምን ከሰማይ ወረድኩ ይለናል አሉት ።
፵፫ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፵፫ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ኢታንጐርጕሩ በበይናቲክሙ ።
እናንት በናንት አትታወኩ አላቸው ።

፵፬ አልቦ ዘይክል መጺአ ኀቤየ እመ ኢሰሐቦ አብ ዘፈነወኒ ።

፵፬ የላከኝ አባቴ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ ካልሰጠኝ በኔ ማመን የሚቻለው የለም ።
ወአነ አነሥኦ በደኀሪት ዕለት በዕለተ ዕርገት አደነዋለሁ ፤ አንድም በጰራቅሊጦስ ።

፵፭ ወሀሎ ጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ ነቢያት ከመ ይከውኑ ኵሎሙ ምሁራነ እምኀበ እግዚአብሔር ። ኢሳ ፶፬ ፣ ፲፫

፵፭ ሁሉ ከእግዚአብሔር ተምረው አዋቆች ይሆናሉ የሚል በመጽሐፈ ነቢያት አለ ። ኢሳይያስ ደቂቅኪ ይከውኑ ምሁራነ በኀበ እግዚአብሔር ያለውን ፤ ኤርምያስ ወኢይምህር እኁ እኅዋሁ እንዘ ይብል አእምርዎ ለእግዚአብሔር እስመ ኵሎሙ የአምሩኒ ንኡሶሙ ወዓቢዮሙ ያለውን ዕንባቆም ትመልእ ምድር እምአእምሮ ስብሐተ እግዚአብሔር ከመ ማይ ዘይደፍን ባሕረ ያለውን ለውጦ አንብበው ። መጽሐፈ ነቢይ ያለ እንደሆነ ኢሳይያስን ብቻ ።

፵፮ ወኵሉ እንከ ዘሰምዓ እምኀበ አቡየ ተምሒሮ ይመጽእ ኀቤየ ። ማቴ ፲፩ ፣ ፳፯

፵፮ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክርልኝ የሰማ ሁሉ ፀውቆ በኔ ያምናል ።
ወአልቦ ዘርእዮ ለአብ ዘእንበለ ዘእምኀቤሁ ለእግዚአብሔር ውእቱ ።
ከርሱ አካል ዘእም አካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ከተወለደ ከልጁ በቀር አብን በባሕርዩ ያየው የለም።
ወውእቱኬ ርእዮ ለአብ ።
እሱን አባቱን አየው እንጂ ።
አንድም ከነቢያት ወገን ልጅ ሁኖ ያየው የለም ልጁ ልጅ ሁኖ አየው እንጂ ።

፵፯ አማን አማን እብለክሙ ዘየአምን ብየ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ።

፵፯ በኔ ያመነ መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል ብየ በውነት እነግራችኋለሁ ።
፵፰ አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ።
፵፰ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ።
፵፱ አበዊክሙሰ መና በልዑ በገዳም ወሞቱ ፣ ዘፀ፣ ፲፮ ፣ ፲፭ ።

፵፱ አባቶቻችሁ መናውን በሉ በምድረ በዳ ክሞት አላዳናቸውም ።

፶ ዝንቱ ውእቱ ኅብስት ዘእምሰማይ ወረደ ከመ ኵሉ ዘበልዓ እምኔሁ ኢይመውት ዘለዓለም ።

፶ ከርሱ የበላ ሁሉ በሥጋ ቢሞት በነፍስ እንዳይሞት ፈርሶ በስብሶ እንዳይቀር ትንሣኤ ዘለ ክብር እንዲነሣ ከሰማይ የወረደ ኅብስት ይህ ነው ።

፶፩ አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እም ሰማይ ።

፶፩ ከሰማይ የወረደ ኅብስት እኔ ነኝ ።
ወዘበልዐ እምዝንቱ ኅብስት የሐዩ ለዓለም ።
ከዚህ ኅብስት የበላም ለዘላለም ሕያው ሁኖ ይኖራል።
ወዝኒ ኅብስት ዘአነ እሁብ ሥጋየ ውእቱ በእንተ ሕይወት ዘለዓለም ።
ሥጋየ በእንተ ሕይወት እሁብ በእንተ ሕይወት ብለህ ግጠም የዘለዓለም ሕይወት ሊሆንእኔ የምሰጠው ኅብስት ሥጋዬ ነውአንድም እኔ የምሰጠው ኅብስት ሥጋዬ ነው ።
በእንተ ሕይወት ዘለዓለም ።
የዘለዓለም ሕይወት ሊሆነው ።

፶፪ ወተገአዙ አይሁድ በበይናቲሆሙ እንዘ ይብሉ እፎ ይክል ዝንቱ የሀበነ ሥጋሁ ንብላዕ ።

፶፪ ሥጋውን እንበላ ዘንድ ሥጋውን መስጠት ይህ እንደምን ይቻለዋል ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ ። እሁበክሙ ቢላቸው እአላፈ እስራኤል ብዙ ነን፤ እንዳንድ ጉርሻ ስንኳን ይደርስናል ብለው፤ ትብልዑ ቢላቸው ማን እገድልሃለሁ ብሎታል ታን ቆን ይሞታል ብለው ፤ ሥጋየ በእንተ ሕይወት ቢላቸው የዕሩቅ ብእሲ ሥጋ ቢበሉት ደሙን ቢጠጡት ደዌ ይሆናል እንጂ ሕይወት ይሆናልን ብለው ።

፶፫ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አማን እብለ ክሙ እመ ኢበላዕክሙ ሥጋሁ ለወልደ ዕጓለ እመ ሕያው ወኢሰተይክሙ ደሞ አልብክሙ ሕይ ወት ላእሌክሙ ።

፶፫ ጌታም የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ለናንተ ሕይወት የላችሁም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ።

፶፬ ዘበልዐ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ።

፶፬ ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የማታልፍ መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል ። ፈረንጆች ደም የሌለው ሥጋ የለም ብለው ሥጋውን ብቻ ያቈርባሉ ይህ ይመሰክርባቸዋል ።
ወአነ አነሥኦ በደኃሪት ዕለት ።
በዕለተ ምጽአት አድነዋለሁ ።

፶፭ እስመ ሥጋየኒ መብልዓ ጽድቅ ዘበአማን ውእቱ ።

፶፭ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ነውና ።
ወደምየኒ ስቴ ሕይወት ውእቱ ።
ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ።

፶፮ ዘበልዐ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ይሄሉ ምስሌየ።
፶፮ ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ ከኔ ጋራ ተዋ ሕዶ ይኖራል ።
ወአነሂ እሄሉ ምስሌሁ ፤
እኔም አድሬበት እኖራለሁ እንደ ብረትና እንደ እሳት የጺጋ ተዋሕዶ ።

፶፯ ወበከመ ፈነወኒ አብ ሕያው ።
፶፯ የላከኝ አብ ሕያው እንደሆነ ።
ወአነሂ ሕያው በእንተ አብ ።
እኔም ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕ ርይ ስለተወለድኩ ሕያው ነኝ ።

፶፰ ወዘበልዐ ሥጋየ የሐዩ በእንቲአየ ።
፶፰ ሥጋዬን የበላ ሥጋዬን ስለበላ ሕያው ሁኖ ይኖራል ።

፶፱ ዝኬ ውእቱ ኅብስት ዘእምሰማይ ወረደ ።
፶፱ የሚገባ ኬ ፤ ከዚያ ሁሉ ቅዱስ ጳውሎስ የብሉዩንና የሐዲሱን ሊቀ ካህናት እያነጻጸረ የሐዲሱን ሊቀ ካህናት እያበለጠ መጥቶ ። ዘከመ ዝኬ ሊቀ ካህናት ይደልወነ እንዳለ ፤ ከዚህም ምድራዊ ውንኅብስትና የሰማያዊው ን ኅብስት እያነጻጸረ ሰማያ ዊውን ኅብስት እያበለጠ መጥቶ ከሰማይ የወረደ ኅብስት ይህ ነዋ ይህ ነው አለ ።
ወአኮ በከመ በልዑ አበዊክሙ መና በገዳም ወሞቱ ።
አባቶቻችሁ መናውን በገዳም በልተውት ከሞት እንዳላዳናቸው ያለ አይደለም ።
ወዘበልዖስ ለዝንቱ ኅብስት የሐዩ ለዓለም ።
ከዚህ ኅብስት የበላ ግን ለዘለዓለሙ ሕያው ሆኖ ይኖራል ።
በእንተ ዕቅፍት ወአልወት ዘእምአርድዕተ ኢየሱስ ።

፷ ወከመዝ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ በም ኵራብ በቅፍርናሆም እንዘ ይሜሀሮሙ ።

፷ በቅፍርናሆም ባለ ምኵራብ ሲያስተም ራቸው ጌታ ይኸን ነገራቸው ።

፷፩ ወብዙኃን እምአርዳኢሁ እለ ሰምዑ ወይ ቤሉ ዕፁብ ዝንቱ ነገር ።

፷፩ ከደቀ መዛሙርቱ ወገን ይኸን ሰምተው ይኸን ነገር ድንቅ ነው ያሉ አሉ ።
ወመኑ ይክል ሰሚዖቶ ።
መስማት ለማን ይቻለዋል አሉ መስማትማ ጆሮ መብረቅስ ይሰማ የለምን ፤ ለብዎቶ ሲል ነው ማወቁ ለማን ይቻለዋል አሉ ።
፷፪ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ በመንፈሱ ከመ አን ጐርጐሩ አርዳኢሁ በእንተ ዝንቱ ።

፷፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሕዝቡ በዚህ ምክንያት እንደታወኩ በአእምሮው ዐውቆ ።
ወይቤሎሙ ዝኑ የአቅፈክሙ ።
ይኸ ይደንቃችኋልን ።
እፎ እንከ እመ ርኢክምዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዘ የዓርግ ኀበ ሀሎ ቀዲሙ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ ቀድሞ ወደነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንደምን በደነቃችሁ ነበር አላቸው ። ምነው ከርደቱ ዕርገቱን አብልጦት ነውን ሁሉስ የአምላክነት ሥራ አይደለምን ቢሉ መሆኑስ ሁሉም የአምላክነት ሥራ ነው ሲወርድ ያየው የለም ሲያርግ ግን ሁሉ ያየዋልና ፤ ሰውም ካላየው ያየውን ማድነቅ ልማድ ነውና ሰው በሚያደንቀው ተናገረ እንጂ አንድም ዝኑ የዐቅፈክሙ እያልክ መልስ ። ይህ ይደንቃችኋል ኋላ አዋሕጀ አሥነሥቼ በመንግሥተ ሰማይ መንፈሳዊ ምግብ ስመግባችሁ ብታዩ እንደምን ባደነቃችሁ ነበር ። ይኸን በምን ያውቁታል ቢሉ ኀብስት አበርክቶ በመመገቡ ፤ አንድም ይህን ይደንቃችኋል ወእፎ እንከ ይህን ዓለም እምኀበ ቦ ኀበ አልቦ ከመኖር ወዳለመኖር ሳላልፈው ብታዩ እንደምን በደነቃችሁ ነበር ። ይኸን በምን ያውቁታል ቢሉ በደረቅ ግምባር ዓይን በመፍጠሩ።

፷፫ መንፈስ ውእቱ ዘያሐዩ ። ዮሐ፡ ፫ ፣ ፲፫።

፷፫ የሚያድን መለኮት ነው ።
ወሥጋስ አልቦ ዘይበቍዕ ወኢምንትኒ ።
ሥጋ ግን አንዳች አይጠቅምም ።
ወዝኒ ቃል ዘአነ ነገርኩክሙ መንፈስ ውእቱ ወሕይወት ውእቱ ።

ይኸም የምነግራችሁ ነገር መለኮት ነው ሕይወት ነው ። እንድም መንፈስ ውእቱ እያልክ መልስ ። የሚያድን መለኮት ነው ። ወሥጋስ ሥጋ ግን አያድንም ። ኅብስትስ መብልዕ ይእቲ አላ ኃይል እንተ ኃደረት ላዕሌሁ ይእቲ ትገብሮ እንዲል ። መብላት የሰውነት ማዳን የመለኮት ነውና ። አንድም የሚያነሣ መለኮት ነው ። ወሥጋስ ። ሥጋ ግን ተነሺ ነው ።

ወኢየንሥእ እመንገለ ሥጋሁ ድኩም አላ በኃይለ እግዚአብሔርእንዲል ። አንድም ዘየሐዩ ብለህ ሦስት ሌሊት ሦስት መዓልት በከርሠ መቃብር ኑሮ የሚነሣ መለኮት የተዋሐደው ሥጋ ነው ። የሩቅ ብእሲ ሥጋ ግን በሦስት ቀን አይነሣም ትንሣኤ ዘጉባኤን ይጠብቃል ። አንድም ዘያሐዩ የሚያድን መንፈሳዊ ትምህርት ነው ወሥጋስ ። ሥጋዊ ትምህርት ግን ምንም ምን አይረባም አይጠቅምም ። ይህም የምነግራችሁ ነገር ረቂቅ ነው ሕይወት ነው።

፷፬ ወባሕቱ ቦ እምውስቴትክሙ እለ ኢየአምኑ ።

፷፬ ነገር ግን ከናንተ ወገን የማያምኑ አሉ ።
እስመ የአምር እግዚእ ኢየሱስ እምትካት ከመ መኑ እሙንቱ እለ ኢየአምኑ ቦቱ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥንት ጀምሮ የማያምኑበት እነማንም እንደሆኑ ያውቅ ነበርና አይሁድ እንደሆኑ ።
ወመኑ ውእቱ ዘይሜጥዎ ።
የሚያሲዘውም ማንም እንደሆነ ያውቅ ነበር ይሁዳ እንደሆነ ።

፷፭ ወእምዝ ይቤሎሙ በእንተ ዝንቱ እብለክሙ አልቦ ዘይክል መጺአ ኀቤየ ለእመ ኢተውህበ ሎቱ እምኀበ አቡየ ።

፷፭ ዕውቀቱ ካባቴ ካልተሰጠው ስለዜህ ነገር በኔ ማመን የሚቻለው የለም ብዬ እነግራችኋለሁ ።

፷፮ ወበእንተ ዝንቱ ነገር ብዙኃን እምአርዳኢሁ እለ ገብኡ ድኅሬሆሙ ወኢሖሩ እንከ ምስሌሁ ።

፷፮ ስለዚህ ማለት እንዲህ ስላላቸው ከሕዝቡ ወገን ከርሱ ጋራ ያልሄዱ ወደኋላቸው የተመለሱ ብዙ ናቸው የተናገረው አይቀርም እያደረገውን አይናገር ብለው ።

፷፯ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለ፲ወ፪ቱ አርዳኢሁ አንትሙኒ ትፈቅዱኑ ትሑሩ ።

፷፯ ዐሥራ ሁለቱን እናንተም ልትሄዱ ትወዳላችሁን አላቸው ። አኒያስ ወደው ተከትለውታል በኃፍ ይነዳቸዋል እንጂ እንዳይሉት አስፈቅዶ ለማስከተል ።

፷፰ ወአውሥአ ስምዖን ጴጥሮስ ።

፷፰ ስምዖን ጴጥሮስም መለሰ ።
ወይቤሎ እግዚኦ ኀበ መኑ ነሐውር እንዘ ቃለ ሕይወት ዘለዓለም ብከ ።
ጌታዬ የዘለዓለም ደኅንነት የሚገኝበት ትምህርት ካንተ ዘንድ እያለ የት እንሄዳለን አለው ።

፷፱ ወንሕነሰ አመነ ወአእመርነ ከመ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልዱ ለእግዚአብሔር ሕያው ።

፷፱ እኛስ አስከ ክርስቶስ ንጉሥ ተብሎ የተነገረልህ የሕያው እግዚአብሔር የባሕርይ ልጁ እንደሆንኸ ዐውቀን አምነናል ።

፸ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ አኮኑ አነ ኀረይኩክሙ ለ፲ወ፪ቱ ። ማቴ፡፲፮ ፣ ፲፮ ማር፡፰ ፣ ፳፱ ሉቃ፡፱ ፣ ፳

፸ ጌታም ዐሥራ ሁለታችሁንማ እኔ መርጫችሁ የለምን ።
ወባሕቱ አሐዱ እምኔክሙ ሰይጣን ውእቱ ።

ነገር ግን ከናንተ አንዱ ሰይጣን ነው ባላጋራዬ ነው አላቸው ፤ ወዓቀመ አዴርሃ ሰይጣነ ላዕለ ሰሎሞን እንዲል ።

፸፩ ወዘንተሰ ዘይቤ እንበይነ ይሁዳ ስምዖን አስቆሮታዊ ይቤ ።

፸፩ ይኽን ነገር የተናገረ የአስቆሮት ሰው ስለሚሆን ስለ ይሁዳ ነው ።
እስመ ውእቱ ሀለዎ ያግብኦ አሐዱ እም፲ቱ ወ፪ቱ ።
ካሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ ያሲዘው ዘንድ አለውና ።

ዘከመ ሖረ ኢየሱስ ኀበ በዓለ መጸለት ።

ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወእምድኅረ ዝንቱ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ገሊላ ።

፩ ከዚህ በኋላ ጌታ ወደ ገሊላ ሄደ ።
ወኢፈቀደ ይሑር ምድረ ይሁዳ ።
ወደ ይሁዳ ሊሄድ አልወደደም ።
እስመ የኃሥሡ አይሁድ ከመ ይቅትልዎ ።
አይሁድ ሊገሉት ይሹታልና ።

፪ ወቀርበ በዓለ መጸለቶሙ ለአይሁድ ።
ዘሌ፡ ፳፫ ፣ ፴፬ ።

፪ አይሁድ ፋሲካቸውን የሚያከብሩበት ቀን ደረሰ ፤ ስለምን መጸለት አለው ቢሉ የተደራረበ በዓል ነው መጸለትን እናከብራለን ሲሉ ቈግር በግብር ምክንያት አስጠርቶ ሮም ወስዷቸዋል ከዚያ ተመልሰው መጸለትን ሳያከብሩ ፋሲካን አያከብሩምና ደራርበው አክብረውታል ። አንድም በግብር ስለ መሰለው ሰው ከበባ ዘንድ ድንኳን ተክለው ጃንጥላ ጥለው ያከብሩታልና ። አንድም በዓለ ናዕት ሲል ነው ጸልቲዮ ይላል ትግሬ ። አንድም በጸያፍ የገባ ነው ።

፫ ወይቤልዎ አኃዊሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ፍልስ እምዝየ ወሑር ምድረ ይሁዳ ።

፫ አኃዊሁ ደቂቀ ዮሴፍ ናቸው ከዚህ ተነሥተህ ወደ ይሁዳ ሂድ አሉት ።
ከመ አርዳኢከኒ ይርአዩ ግብረከ ዘትገብር ወይእመኑ
የምትሠራውን ተአምራት አይተው ሕዝቡ ያምኑብህ ዘንድ ከጉባኤው ከዋለ ደቂ መዝሙር ማለት ልማድ ነው ።

፬ እስመ አልቦ ዘይገብር ምንተኒ ጽሚተ ወይፈቅድ ክሡተ ይኩኖ ።

፬ እንዘ ይፈቅድ በል ሥራው ሊገለጥ ወዶ ሳለ ሥራውን ሰውሮ ምንም ምን የሚሠራ የለምና ። አንተም ሥራህ ሊገለጽልህ ትወዳለህና ። አንድም እስመ አልቦ ዘይገብር ወኢምንተኒ ጽሚተ ወኢይፈቅድ ክሡተ ይኩኖ ። ሥራውን ምንም ምን ሰውሮ የሚሠራ የለምና ሊገለጽለትም የማይወድ የለምና ፣ አንተም ሥራህ ሊገለጽልህ ትወዳለህና ። አንድም እስመ አልቦ ዘኢይገብር ፣ ሥራውን ምንም ምን ሰውሮ የማይሠራ የለምና ፤ ወይፈቅድ ሊገለጽበትም የሚወድ የለምና አንተ ግን ሊገለጽልህ ትወዳለህና ። አንድም እስመ አልቦ ዘኢይገብር ወኢይፈቅድ ፤ ሥራውን ምንም ምን ሰውሮ የማይሠራ ሊገለጽለትም የማይወድ የለምና አንተም ሊገለጽልህ ትወዳለህና ።
ወእመሰ ዘንተ ምግባረ ትገብር አርኢ ርእሰከ ለዓለም ።
ይህን የምታደርግ ከሆነ አምላክነትህን ለሁሉ ግለጽ።

፭ እስመ አኃዊሁኒ ኢአምኑ ቦቱ ።

፭ ወንድሞቹ ደቂቀ ዮሴፍ አላመኑምና እንዲህ አሉ ።

፮ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ጊዜየ ዓዲ እስከ ይእዜ ኢበጽሐ ።

፮ ጌታም እኔ የምወጣበት ጊዜ አልደረሰም ።
ወጊዜ ዚአክሙሰ ዘልፈ ድልው ውእቱ ።
የናንተ ጊዜ ዘወትር የተዘጋጀ ነው ማለት እናንተ ግን የምትወጡበት ጊዜ ደርሷል የተደራረበ በዓል ነው ቢሉ ጌታ የሚወጣ ለበዓለ ፋሲካ ነው እንጂ ለበዓለ መጸለት አይደለምና ። በዓለ ፋሲካ ነው ቢሉ ጌታ የሚወጣ ለማስተማር ነው እንጂ ለገቢረ በዓል አይደለምና ። አንድም በኔ ሳላውቀው ሞት አይመጣብኝም በናንተ ግን ሞት ሳታውቁት ሞት ይመጣባችኋል ።

፯ ኢይክል ዓለም ጸሊኦተክሙ ።
፯ እናንተን ሰው አይጠላችሁም ።
ወሊተሰ ይጸልኡኒ ።
እኔን ግን ይጠሉኛል ።
እስመ ስምዕ ላዕሌሆሙ ።
እኔ እመሰክርባቸዋለሁና ።
ወእዛለፎሙ በከመ እኩየ ምግባሮሙ ።
እንደ ሥራቸው ክፋት ፤ አንድም በክፉ ሥራቸው እዛለፋቸዋለሁና እሴ ለክሙ ጸሐፍት ፈሪሳውያን እያልኩ ።

፰ አንትሙሰ ዕርጉ ውስተ ዝንቱ በዓል ።

፰ እናንተ ወደዚህ በዓል ውጡ ።
ወአንሰ ኢየዓርግ ይእዜ ውስተ ዝንቱ በዓል ።
እኔ ግን ወደዚህ በዓል ዛሬ አልወጣም ።

እስመ ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜየ ።
የምመጣበት ጊዜ ገና አልደረሰምና ።

፱ ወከመዝ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ነበረ ውስተ ገሊላ ።

፱ ተርፈ ሲል ነው ወነበረ ውስተ ኢየሩሳሌም እንዲል ። ይኽን ነግሯቸው በገሊላ ቀረ ።

፲ ወዓሪጎሙ አኃዊሁ ለበዓል ውእተ አሚረ ዓርገ ውእቱኒ ጽሚተ ወአኮ ገሃደ ።

፲ ዶቂቀ የሴፍ ከወጡ በኋላ እርሱም ተገልጦ ያይደለ ተሰውሮ ወጣ ።

፲፩ ወአኃዙ አይሁድ ይኅሥሥዎ በበዓል ።

፲፩ አይሁድ በበዓል ይሹት ጀመር።
ወይቤሉ አይቴ ውእቱ ዝኩ ።
ያ የት ነው ያለ አሉ ፤ ዝኩ ቃለ ጸብዕ ነው ዝኩ ወልደ ሰሴይ እንዲል ።

ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ ገሃደ በእንተ ተፈንዎቱ መለኮታዊ ።

፲፪ ወብዙኃን እንጕርጕሩ ሕዝብ በእንቲአሁ።
፲፪ ሕዝቡም በርሱ ምክንያት ፈጽመው ታወኩ
ወቦ እለ ይቤሉ በእንቲአሁ ኄር ውእቱ ።
ደግ ነው ያሉ አሉ ።
ወካልዓን ይቤሉ አልቦ ።
ደግም አይደለ ያሉም አሉ ።
አላ ያስሕቶሙ ለሕዝብ ።
ሕዝቡን ያስታቸዋል እንጂ ሊያስታቸው ነው እንጂ።

፲፫ ወባሕቱ ክሡትሰ አልቦ ዘተናገረ በእንቲአሁ በእንተ ፍርሃቶሙ ለአይሁድ ።

፲፫ ነገር ግን አይሁድን ስለፈሩ ኄር ውእቱ ማለትን ገልጦ የተናገረ የለም ።

፲፬ ወበማእከለ በዓል ዓርገ እግዚእ ኢየሱስ ምኵራበ ወአኃዘ ይምሐር ።

፲፬ የተደራረበ በዓልነው ቢሉ በዓለ መጸለት አልቆ በዓለ ፋሲካ ሲጀመር በዓለ ፋሲካ ነው ቢሉ በአራተኛው ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከምኵራብ ገብቶ ያስተምር ጀመር ።
፲፭ ወአንከሩ አይሁድ ምሀሮቶ እንዘ ይብሉ ዝንቱ እፎ የአምር መጽሐፈ ዘኢመሀሮ መኑሂ ።
፲፭ የበጐ አንክሮ ፤ ማንም ማን ያላስተማረው

ይህ መጽሐፍን እንደምን ያውቃል ብለው አደነቁ ።

እንድም ማንም ማን መጽሐፍን ያስተማረው የሌለ ይህ እንደምን ዓውቃለሁ ይላል ብለው አደነቁ ይህ ሠራርቹ አሉት ።

፲፮ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ትምህርትየሰ ኢኮነት እንቲአየ አላ እንቲአሁ ለዘፈነወኒ ።

፲፮ ትምህርቴ የኔ አይደለችም የላከኝ ያባቴ ናት እንጂ ። እንድም የኔ ብቻ አይደለችም የላከኝ ያባቴም ናት እንጂ ።

፲፯ ወዘሰ ይፈቅድ ይግበር ሥምረቶ ውእቱ ይቅድም ወያእምር ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ትምህርትየ ።

፲፯ ያባቴን ፈቃድ ሊያደርግ የወደደ ትምህርቱ ከእግዚአብሔር እንደ ተገኘች ያውቃል ።
ወአኮ ዘእምኀቤየ እነግር ።
ከኔ እንዳልተገኘ ። እንድም ከኔ ብቻ እንዳልተገኘ ከእግዚአብሔርም እንደ ተገኘ ያውቃል ።
፲፰ ወዘሰ ለሊሁ ዘእምኀቤሁ ይነግር ተድላ ርእሱ የኃሥሥ
፲፰ ከራሱ አንቅቶ የሚያስተምር ግን ራሱን

ደስ ሊያሰኝ ይወዳል ። ለልየኑ እነግር ለርእሰየ ዘሰ ለርእሱ ይነግር ተድላ ርእሱ የኃሥሥ ይላል ።
ወዘሰ ይፈቅድ ያድሉ ለዘፈነዎ ጻድቅ ውእቱ ።
ላኪውን ደስ ሊያሰኝ የሚወድ ግን እውነተኛ ነው ።
ወአልቦ ዓመፃ በኀቤሁ ።
በርሱም ሐሰት የለበትም ፤ እንድም ላኪየን ደስ ላሰኝ የምወድ እኔ የባሕርይ አምላክ ነኝ ብዬ ባስተምር ሐሰት አላስተምርም ።

፲፱ አኮኑ ሙሴ ወሀበከሙ ኦሪተ ።
ዘፀ ፳፬ ፡ ፫ ።

፲፱ ሙሴ ኦሪትን ሠርቶላችሁ የለምን ።
ወኢ፩ሂ እምኔክሙ ኢትገብርዋ ለኦሪት ።
ከናንተ አንዱ ስንኳ ኦሪትን አይሠራትም እንድም አንዳችሁ ስንኳ ኦሪትን አትሠሩዋትም ። እንድም አልቦ ዘይገብራ ። የሚሠራት የለም ።

፳ ለምንት እንከ ተኃሥሡ ወትፈቅዱ ትቅትሉኒ ።

፳ ኦሪትን የማንሠራት እንደምን ነው ትሉኝ እንደሆነ ኦሪት ኢትቅትል ጻድቀ ትላለች ጻድቅ እኔን ልትገድሉኝ ለምን ትሻላችሁ ።

፳፩ ወአውሥኡ ሕዝብ ወይቤልዎ ጋኔንኑ ብከ
፳፩ ሕዝቡም መለሱ ሎቱ ስብሐት ጋኔን አድሮብሃልን ።
መኑ የኃሥሥ ይቅትልከ ።
ማን ሊገድልህ ይሻሃል አሉት ።
ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታም መለሰ ።

ወይቤሎሙ ፩ደ ግብረ ገበርኩ ።
አንድ ሥራ ሠራሁ ጕሕቈትን መጻጕዕን ፈወስኩ ።
ወዅልክሙ አንክርክሙኒ ።
ለጊዜው ሁላችሁ አደነቃችሁኝ ።

፳፪ በእንተ ዝንቱ ወሀበክሙ ግዝረተ ።
ዘሌ፡፲፪ ፡ ፫ ዘፍ፡፲፯ ፡ ፲ ።

፳፪ ስለዚህ ማለት ጥንቃቄ አይሁድስ እንዳይሆን ሙሴ ግዝረትን ሠርቶላችኋል ።
ወኢኮነት እምኀበ ሙሴ ፤
እፎ የአምር ዝንቱ መጽሐፈ ዘኢመሐሮ መኑሂ ብለውት ነበርና ታሪክ አያውቅም እንዳይሉት ነገር ግን በሙሴ አልተጀመረችም ።
አላ እምአበው ይእቲ ፤
በነአብርሃም ነው እንጂ ።
ወበሰንበት ትገዝርዎ ለሰብእ ።
ቅዳሜ የተወለደውን ቅዳሜ ትገዝሩታላችሁ ።

፳፫ ወእመሰ በሰንበት ግዝረተ ይነሥእ ብእሲ ከመ ኢይሠንር ሕጉ ለሙሴ ፤

፳፫ ዘኢተገዝረ ክቱማ ነፍስቱ አመ ሳምንት ዕለት ብላ አሪት ።
የተናገረችው እንዳይፈርስ ቅዳሜ የምትገዝሩት ከሆነ ለምንት እንከ ሊተ ትግዕዙኒ ለእመ አሕየውክዎ ለብእሲ ዅለንታሁ በሰንበት ።
የሰውን ሁለንታ ሥጋውን በተአምራት ሁለንታ ነፍሱን በትምህርት ቅዳሜ ባድነው ለምን ትነቅፉኛላችሁ ።

፳፬ ኢትፍትሑ በአድልዎ ።
፳፬ በግብዝነት በሐሰት አትፍረዱ ። ዘዳ፡ ፩ ፡ ፲፮

አላ ፍትሐ ጽድቅ ፍትሑ ።
በሚገባ በውነት ፍረዱ እንጂ ሰንበትን መሻር ይሆታ ምላጩ ሲለመጥ ሥጋው ሲቆረጥ ደሙ ሲፈስ ፤

፳፭ ወቦ እለ ይቤሉ እምሰብአ ኢየሩሳሌም አኮኑ ዝንቱ ዘየኃሥሡ አይሁድ ይቅትልዎ ።

፳፭ በኢየሩሳሌም ካሉ ሰዎች ወገን አይሁድ ሊገድሉት የሚሹት ይኸ አይደለምን ።

፳፮ ወናሁ ገሀደ ይትናገሮሙ ።
፳፮ እነሆ ቃል ለቃል ይነጋገራቸዋል ።
ወእልቦ ዘይቤልዎ ምንተኒ ።
ምንም የመለሱለት ምላሽ የለም ያሉ አሉ ።
አእመሩኑ እንጋ መላእክት ወሊቃውንት ከመ ዝንቱ ውእቱ ክርስቶስ በአማን ።
ሊገሉት የሚሹት እርሱ እንደሆነ አለቆቹ አውቀው ንቀው ትተውታልና አሉ ። አንድም እስክ ክርሰቶስ ንጉሥ ተብሎ የተነገረለት እርሱ እንደሆነ በውነት አውቀው እምነውበታልን አሉ ።

፳፯ ወባሕቱ ለዝንቱሰ ነአምሮ እምአይቴ ውእቱ ።

፳፯ ነገር ግን ይኸን ከወዴትም እንደመጣ እናውቃለን ።
ወክርስቶስሰ አመ ይመጽእ አልቦ ዘየአምሮ እምኀበ ይመጽእ ።
ክርስቶስ ግን በመጣ ጊዜ የመጣበትን የሚያውቅ የለም የዕዝራ ነገር ትዝ ብሏቸው ፤
ወርኢኩ ዓቢይ ነፋስ ይወፅእ እምባሕር እንዲል ።
ከባሕር ጥቅል ነፋስ ሲወጣ አይቷል ወዲያው መልአኩ ይህ የመጣበት እንዳይመረመር ክርስቶስበመጣ ጊዜ የሚመረምረው የለም ብሎታል ።

፳፰ ወአልዐለ ቃሎ እግዚእ ኢየሱስ በምኵራብ እንዘ ይሜህሮሙ ።

፳፰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምኩራብ ሲያስተምር ቃሉን አሰምቶ ተናገረ ።
ወይቤሎሙ ኪያየኒ ተአምሩ ።
እኔን ታውቁኛላችሁን ።
ወተአምሩኑ እምአይቴ መጻእኩ አነ ።
ከወዴትም እንደመጣሁስ ታውቃላችሁን ።
ወእኮ ሰልየ ኢመጻእኩ ።
በኔ ፈቃድ ብቻ ሰው ልሆን አልመጣሁም ።
አላ ሀሎ ጻድቅ ዘፈነወኒ ።
በላከኝ ባባቴ ፈቃድ ነው እንጂ ፤
ዘኢተአምርዎ አንትሙ ።
እናንተ የማታውቁት ።

፳፱ ወአንሰ አአምሮ ።
፳፱ እኔ ግን አውቀዋለሁ ።
እስመ እምኀቤሁ አነ ፤
ከርሱ እካል ዘእምአካል ተወልጃለሁና ።
ወውእቱ ፈነወኒ ።
በርሱ ፈቃድ ሰው ሁኛለሁና ።

፴ ወፈቀዱ የአኀዝዎ ።
፴ ሊይዙት ወደዱ ።
ወባሕቱ አልቦ ዘአንሥአ እዴሁ ላዕሌሁ ።
ነገር ግን በጠላትነት እጁን ያነሣበት የለም ።
እስመ ዓዲሁ ኢበጽሐ ጊዜሁ ።
የሚሞትበት ጊዜ ገና አልደረሰምና ።

፴፩ ወእምውእቶሙ ሰብእ ብዙኃን እለ አምኑ ቦቱ ።

፴፩ በዚያ ካሉ ሰዎች ያመኑበት ብዙ ናቸው ብዙ ሰዎች አመኑበት ።
ወይቤሉ አመ ይመጽእ ክርስቶስ ቦኑ ፈድፋደ ተአ

ምረ ዘይገብር እምዘገብረ ዝንቱ ።
በውኑ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ይህ ሰው ካደረገው ተአምራት የሚበልጥ የሚያደርገው ተአምራት አለን አንድም የበለጠ ተአምራት ያደርጋል አሉ ።

፴፪ ወሰሚዖሙ ፈሪሳውያን ከመ እንጐርጐሩ ሕዝብ በእንቲአሁ ።

፴፪ ፈሪሳውያን ሕዝቡ በርሱ ምክንያት እን ዳዘኑ ሰምተው ።
ፈነወ ሊቃነ ካህናት ወፈሪሳውያን ወእልያኒሆሙ ከመ የአኃዝዎ ።
ይህ ሁሉ እኛ ዝም ብንል አይደለም ብለው ፈሪሳውያንና የካህናት አለቆች ያዙ ብለው ብላቴኖቻቸውን ላኩ ።

፴፫ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ዓዲ ኅዳጠ መዋዕለ ሀሎኩ ምስሌክሙ ።

፴፫ ጌታም ገና ጥቂት ቀን ከናንተ ጋራ እኖራለሁ ።
ወእምዝ አሐውር ኀበ አብ ዘፈነወኒ ።
ከዚህ በኋላ ወደላከኝ ወዳባቴም እሄዳለሁ ።

፴፬ ተኃሥሡኒ ወኢትረክቡኒ ። ዮሐ፡፲፫፡ ፴፫
፴፬ ትሹኛላችሁ አታገኙኝም ።
ወኀበ እነ አሐውር አንትሙ ኢትክሉ መጺአ ።
እኔ ወደምሄድበት መምጣት አይቻላችሁምና ።
አንድም ተኃሥሡኒ እያልክ መልስ ። በፈቃዱ የምሞተውን ሞት በግድ እንገድለዋለን ብላችሁ ትሹኛላችሁ ። ወኢትረክቡኒ አታገኙኝም በፈቃድ የምሞተውን ሞት በግድ መግደል አይቻላችሁምና። አንድም በጽድቀ አብርሃም ያጸድቀናል ብላችሁ ትሹኛላችሁ አታገኙኝም ፤ እኔ በተሰቀልኩበት መስቀል ተሰቅላችሁ እኔ በሞትኩበት ሞት ሞታችሁ እኔ ከገባሁበት ውሣጤ መንጦላዕት ገብቶ መኖር አይቻላችሁምና ። አንድም ዓመተ ቃይናንን ፍቃችሁ እንደገና ይወርዳል ይወለዳል ብላችሁ ትሹኛላችሁ ፤ አታገኙኝም ከዚህ ቀድሞ የተወለደው እርሱ አይደለም ብሎ ማመን አይቻላችሁምና ፤ አንድም በጥጦስ ጊዜ እግኝተነው ተአምራት አድርጎልን ብላችሁ ትሹኛላችሁ አታገኙኝም ፤ ዛሬም ብናምንበት ይሆን የለም ብሎ ማመን አይቻላችሁም ።

፴፭ ወይቤሉ አይሁድ በበይናቲሆሙ አይቴኑ ሀለዎ ለዝንቱ ይሑር ዘኢንክል ረኪቦቶ ንሕነ ።

፴፭ አይሁድ እርስ በርሳቸው እኛ የማናገኘው ለዚህ ወዴት ይሄድ ዘንድ አለው አሉ ።
ውስተ ብሔረ አረሚኑ የሐውር እንጋ ወይሚህሮሙ ለአረሚ ።
አንዳች ግዙፉ ሥርዓት አፍርሶ ወደ አረማውያን ሄዶ አረማውያንን ያስተምር ዘንድ አለውን ።

፴፮ ምንትኑ ዝንቱ ነገር ዘይብለነ ተኀሥሡኒ ወኢትረክቡኒ ።

፴፮ ትሹኛላችሁ አታገኙኝም ።
ወኀበ እነ አሐውር አንትሙ ኢትክሉ መጺአ ።
እኔ ወደምሄድበት መምጣት አይቻላችሁም የሚለን ነገር ምንድር ነው ።

ዘከመ ከሠተ ኢየሱስ መንፈሰ ቅዱስ ።

፴፯ ወበደኀሪት ዕለት ዘበዓል ዓባይ ቆመ እግዚእ ኢየሱስ ከልሐ ወይቤ ዘጸምዓ ይምጻእ ኀቤየ ወይስተይ ። ዘሌ፡፳፫ ፡ ፴፮ ።

፴፯ እስመ ይእቲ ዘዐአት ይላታል ።
በአራት ዘመድ ከዘመዱ ወዳጅ ከወዳጁ የተረፉቸውን ስንቃቸውን በልተው የሚለያዩበት ናት በየ ሀገራቸው ለመሄድ በዚህ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሻ በኔ ይመን ልጅነትንም ያግኝ ብሎ አሰምቶ ተናገረ ።

፴፰ ወዘሂ የአምን ብየ በከመ ይቤሉ መጻሕፍት አፍላገ ማየ ሕይወት ዘይውኅዝ እምከርሡ ኢሳ፡፶፰፡፲፩

፴፰ መጻሕፍት ጻድቅኒ በአሚን የሐዩ ወዘሉ ዘጸውዓ ስመ እግዚአብሔር ይድኅን ብለው መጻሕፍት እንደ ተናገሩ በኔ ካመነ ሀብታት ምሥጢራት ከሱ ይገኛሉ ። አንድም ዘጸምዓ ብለህ መልስ የሻ በኔ ይመን ልጅነትንም ያግኝ ። ወዘሂ የአምን ብየ ዝርዝሩን ለጌታ ሰጥ ኢሳይያስ እነ እነቅዕ አፍላገ በውስተ በድው ወይውኅዝ ማይ በውስተ በድው ወይረውዩ ጽሙዓን ወይከውን ብሔርከሙ አፍላገ ማይ ወይውሕዝ ማይ ርጊብ ወስፉሕ ወእለ ጸምዑ ይሑሩ ኀበ ማይ ወይስተዩ ዘእንበለ ወርቅ ። ኤርምያስ ኀደጉኒ ሊተ ነቅዓ ማየ ሕይወት ወከረዩ ሎሙ ዓዘቅተ ዘኢይትረከብ ማዩ ። ዘካርያስ ማየ ሕይወት ዘይውኅዝ እምኢየሩሳሌም መንፈቁ መንገለ ባሕር ቀዳሚት ፤ ወመንፈቁ መንገለ ባሕር ደኀሪት ። ሆሴዕ በጥሬው ወልድ ጠቢብ ዘኢያጠብዕ በሞተ ውሉድ ዕሜተ እብ እፍላገ ማየ ሕይወት ይውኅዝ እምከርሡ ብለው መጻሕፍት እንደተናገሩ ሀብታትም ሥጢራት ከኔ ይገኛሉና የሻ በኔ ይመን ልጅነትን ያግኝ ።

፴፱ ወዘንተ ዘይቤ በእንተ መንፈስ ቅዱስ ዘሀለዎሙ ይንሥኡ እለ የአምኑ ቦቱ ። ኢዩ፡፪፡ ፳፰ ግብ፡፪ ፡ ፲፯ ።
፴፱ በርሱ ያመኑ ምእመናን ይቀበሉት ዘንድ ስላላቸው ስለመንፈስ ቅዱስ ይኸን ተናገረ ።
እስመ ዓዲ ኢወረደ መንፈስ ቅዱስ በእንተ ዘኢተሰብሐ ዓዲሁ እግዚእ ኢየሱስ ።

ጌታ ገና ስላልተሰቀለ መንፈስ ቅዱስ ገና አልተሰጠ ምና ።

ዘከመ ሐለዩ አይሁድ ላዕለ ኢየሱስ ዘዘዚአሆሙ ሐልዮታተ ።

፵ ወብዙኃን እምሕዝብ ሰሚዖሙ ዘንተ ነገረ ይቤሉ አማን ነቢይ ውእቱ ዝንቱ ።

፵ ከሕዝቡ ወገን ብዙዎቹ ይህን ሰምተው ነቢይ ነው አሉ ።

፵፩ ወቦ ይቤሉ ክርስቶስ ውእቱ ።
፵፩ ተሻልን ያሉት ልዩ ልዩ መስሏቸው ክርስቶስ ነው ያሉም አሉ ።
ወመንፈቆሙ ይቤሉ ቦኑ እምገሊላ ይመጽእ ክርስቶስ ።
ዓወቅን ጠነቀቅን ያሉ ጻሐፍት ፤ ፈሪሳውያን ግን በውኑ ክርስቶስ ከገሊላ ይነሣልን አሉ ።

፵፪ አኮኑ ይብል መጽሐፍ ከመ እምዘርዐ ዳዊት ወእምነ ቤተ ልሔም ሀገሩ ለዳዊት ይመጽእ ክርስቶስ ፤ ሚክ· ፭፡፪ ማቴ፡ ፪፡፮ ።

፵፪ ከዳዊት ወገን ከዳዊት አገር ከቤተልሔም ክርስቶስ እንዲወለድ መጽሐፍ ተናግሮ የለም አሉ ። መካህ ይወፅእ እምኤዶም ያለውን መተርጐም ወይ እቲ ኤዶም እምአድያማተ ገሊላ ብሎ እንደ ተረጐመው ባያውቁ ።

፵፫ ወተገዓዙ ወተናፈቁ ሕዝብ በበይናቲሆሙ በእንቲአሁ ።

፵፫ ሕዝቡ በርሱ ምክንያት እርስ በርሳቸው ተለያዩ ተከራከሩ ።

፵፬ ወቦ እለ ፈቀዱ የአኃዝዎ ።
፵፬ ሊይዙት የወደዱም አሉ ።
ወባሕቱ አልቦ ዘአንሥአ እዴሁ ።
ነገር ግን ማንም እጁን አላነሣበትም ።

፵፭ ወተሠውጡ አልከቱ ወዓሊያኒሆሙ ኅበ ሊቃነ ካህናት ወፈሪሳውያን ።

፵፭ ብላቴኖቻቸው ወደሊቃነ ካህናትና ወደ ፈሪሳውያን ተመለሱ ።
ወይቤልዎሙ እሙንቱ እፎኑመ ዘኢያምጻእክምዎ ።
እርስ በርሳቸውም ምነው ያላመጣችሁት አሏቸው ።

፵፮ ወአውሥኡ ወዓልያኒሆሙ ።
፵፮ ብላቴኖቻቸውም መለሱ ።
ወይቤልዎ ግሙራ ኢተናገረ ሰብእ ዘከመ ተናገረ ውእቱ ብእሲ ።
ያሰው እንደተናገረው ፤ ያለ ነገር ከቶ ሰው ተናግሮት አያውቅም አሏቸው ።

፵፯ ወአውሥኡ ፈሪሳውያን ።
፵፯ ፈሪሳውያንም መለሱ ።
ወይቤልዎሙ ትጌግዩኑ አንትሙኒ ።
እናንተም ታስታላችሁን አሏቸው ዋዌው ለሐዋርያት ነው ።

፵፰ ቦኑ እመላእክት ወእምፈሪሳውያን ዘአምነ ቦቱ ።

፵፰ ወይስ ካለቆች ከፈሪሳውያንም ወገን ያመነበት አለ ።

፵፱ ዘእንበለ እሉ ጊጉያን ሕዝብ እለ ኢያአምሩ ኦሪተ ።

፵፱ ኦሪትን ከማያውቁ ከኒህ ስሁታን በቀር ።
ወእሙንቱሰ ርጉማን ፤ እነሱ ግን የተረገሙ ናቸው ።

፶ ወይቤሎሙ ኒቆዲሞስ ዘሖረ ኀቤሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ቀዲሙ ሌሊተ አሐዱ እምኔሆሙ ዮሐ ፫ ፪ ።

፶ አስቀድሞ በሌሊት ወደ ጌታ የሄደ ከርሳቸው አንዱ ኒቆዲሞስ አላቸው ።

፶፩ ኦሪትክሙኑ ትኴንኖ ለሰብእ ዘእንበለ ይሕትትዎ ቅድመ ወያእምሩ ምግባሮ ዘገብረ ዘዳ፡፲፱፡፲፮ ።

፶፩ ኦሪትነኑ ሲል ነው በእንተ ክብርክሙ እንዲል ። ከርሳቸው ወገን የሚሆን አስቀድሞ በሌሊት ወደ ጌታ የሄደ ኒቆዲሞስ ኦሪታችን ሥራውን አስቀድሞ መርምሮ ሳያውቁ ፍረዱበት ትላለችን አላቸው ። አንድም እርሱ አምኑዋልና ። ኦሪትክሙኑ ይላል ።

፶፪ ወአውሥእዎ ወይቤልዎ አንተኒ እምገሊላኑ ትብል አንተ ።

፶፪ አንተም ዐዋቂው እንዳላዋቂ ትሆናለህ አሉት ።
ኅሥሥ መጽሐፈ ወትርኢ ከመ እምገሊላ ኢይትነሣእ ነቢይ ፤
ነቢይ ከገሊላ እንዳይነሣ ከመጽሐፍ ሻ መርምር ።

፶፫ ወገብኡ ኵሉ ለለ አሐዱ ውስተ ቤቶሙ ።
፶፫ ሁሉም እያንዳንዳቸው ወደቤታቸው ተመለሱ ። ሻ መርምር ብለውታልና ሊሹ ሊመረምሩ ፤ አንድም እርስ በርሳቸው ተጃመሩ ይሉናል ብለው ። አንድም ነገራቸው ቢፈርስባቸው ብላቴኖቻቸው ግሙራ ኢተናገረ ሰብእ ዘከመ ተናገረ ውእቱ ብእሲ አሉ ፤ ኒቆዲሞስ ኦሪትክሙኑ ትኴንኖ ለሰብእ አለ ።

በእንተ ዘማዊት ብእሲት ።

ምዕራፍ ፰ ።

፩ ወኢየሱስኒ ሖረ ውስተ ደብረ ዘይት ።
፩ ጌታ በምዕራብ ሲያስተምር ውሎ አዳሩን

ወደ ደብረ ዘይት ሄደ ።

፪ ወእንግህ በጽባሕ ወቦአ ካዕበ ምኵራበ ፤
፪ ወኮነ መዓልተ ይሜህር በምኵራብ ወሌሊተ ይበይት ውስተ ደብረ ዘይት እንዲል ፤ ሌሊት በደብረ ዘይት ሲጸልይ ያድራል ፤ ቀን በምኵራብ ሲያስተምር ይውል ነበርና ማለዳ ገሥግሦ ወደምኵራብ ሄደ ።
ወተጋብኡ ኵሉ ሕዝብ ኀቤሁ ።
ሕዝቡ ሁሉ ወደርሱ መጡ ።
ወነበረ ይምሀሮሙ ።
በትምህርት ተገኘላቸው ። ወአኀዘ ይምሀሮሙ ይላል ያስተምራቸው ጀመር ፤ ትምህርቱ ብፁዓን ነው ፤ አንድም ሌላ ።

፫ ወአምጽኡ ኀቤሁ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ብእሲተ እስርተ እንተ ተረክበት በዝሙት ።

፫ ጸሐፎችም ፈሪሳውያንም በሴሰኝነት ተይዛ የታሰረች ሴት ወደርሱ አመጡ ።
ወአብእዋ ውስጠ ወአቀምዋ ቅድመ እግዚእ ኢየሱስ ።
ከውስጥ አግብተው ጌታ ካለበት አቀረቧት ። ዕለቱን ነው ቢሉ አንዱን ቅጥር አግብተው በሦስተኛው ቀን ነው ቢሉ ሁለቱን ቅጥር አግብተው ።

፬ ወይቤልዎ ሊቅ ረከብናሃ ለዛቲ ብእሲት በዝሙት እንዘ ትዔብስ ።

፬ መምህር ሆይ ይህች ሴት በሴሰኝነት አግኝተናታል ።

፭ ወበሕግነስ ሠርዓ ሙሴ ከመ ትትወገር በአብን ፤ ዘሌ. ፳፥፲ ።

፭ እንደኛ ሥርዓት ሙሴ በደንጊያ ተወግራ ትሙት ብሏል ።
ወአንተ እንከ ምንተ ትብል በእንቲአሃ ።
አንተስ የእርሷን ነገር ምን ትፈርዳለህ አሉት ።
እስመ ናሁ ተረከበት በዝሙት ።
በሴሰኝነት ተገኝታለችና ፤

፮ ወዘንተ ይቤሉ እንዘ ያሜክርዎ ።
፮ ሲፈትኑት እንዲህ አሉት ።
ከመ ይርከቡ በላዕሌሁ ምክንያተ ።
ምክንያት ያገኙበት ዘንድ ትምህርቱ ብፁዓን ነው ቢሉ አትሙት ቢል ወኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ ዘእንበለ ትዘሙ በላዕሌሁ ለሊሁ ረሰያ ዘማ ይላል ። አንድ ጊዜ እንዲህ ይላል ነገሩ ቀዋሚ አይደለ ምሳ ለማለት ። ትወገር ቢል የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ይላል የሰው ጥፋት አያሳዝነውም ለማለት ትምህርቱ ሌላ ነው ቢሉ ትወገር ቢል ። አንሰ ኢመጻእኩ ለኰንኖ ዝንቱ ዓለም ይላል ፤ አንድ ጊዜ እንዲህ ይላል ነገሩ ቀዋሚ አይደለምሳ ለማለት ። አትወገር ቢል የሙሴን ሥርዓት አፈረሰ ብለው እንማላቀቃለን ብለው ።
ወአትሐተ እግዚእ ኢየሱስ አዕይንቲሁ ውስተ ምድር ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኖራ ኖራውን ተመለከተ ።
ወጸሐፈ በአፅባዕቱ ።
ቀረጸውም ።

፯ ወሶበ ቆሙ ብዙኃን ወአጐንደዩ ተስእሎቶ አንሥአ አዕይንቲሁ ዘዳ፥ ፲፯፥፯ ።

፯ ቆመው መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ዐይኑን አቀና ።
ወይቤሎሙ ዘአልቦ ኃጢአት እምኔከሙ ቀዲሙ ለይገራ በእብን ።
ከናንተ ወገን እርሷ የሠራችውን ኃጢአት ያልሠራ ሰው ደንጊያ ይጣልባትና ከዚያ በኋላ ግደሏት አላቸው ። ኖራውን በቀረጸው ጊዜ ኃጢአታቸው በየግንባራቸው እየተጻፈ ታይቷል ይህስ እንዳይሆን ከባቴ አበሳ ነው ያንዱን ኃጢአት አንዱ ይይበት ብሎ እንዲህ አያደርግም የአንዱ ኃጢአት ባንዱ ግንባር የአንዱ ኃጢአት ባንዱ ግንባር እየተጻፈ ታይቷል ።

፰ ወካዕበ ደነነ ዲበ ምድር ።
፰ ሁለተኛም ወደ ምድር አየ ።
ወጸሐፈ በአፅባዕቱ ፤
ቀረጸው ። የነቢቡን የገቢሩን የሐልዮውን ለማለት ደገመው ።

፱ ወሰሚዖሙ እሙንቱ ዘንተ ዘለፋ በለብዎ አኀዙ ይሑሩ በበአሐዱ እስከ ወፅኡ ሊቃውንቲሆሙ እምቀዳሚ እስከ ደኃሪ ።

፱ ዘአልቦ ኃጢአት ያለውን ሰምተው የሰው ኃጢአት እንገልጣለን ብለን ኃጢአታችንን ገለጠብን ብለው ፊት ከገቡት በኋላ እስከ ገቡት በውስጥ ካሉት በአፍአ እስካሉት እምሊቅ እስከ ደቂቅ እንዲሉ ወጥተው ሄዱ ።

ወተርፈ እግዚእ ኢየሱስ ባሕቲቱ ።
ጌታ ብቻውን ቀረ ። ንጹሐ ባሕርይ ነውና ።
ወይእቲኒ ብእሲት ትቀውም ውስጠ ።
እርሷም ቁማ ቀረች ፤ ለጊዜው ።
ተኃድግ ለኪ ኃጢአትኪ የሚላት ነውና ።

፲ ወአንሥአ ኢየሱስ አዕይንቲሁ ወነጸረ ኀቤሃ ።

፲ ኢየሱስም ዓይኑን አቅንቶ ወደርሷ አየ ። ወይቤላ ኦ ብእሲቶ አይቴ ሀለዉ እለ ይኴንኑኪ ። አንች ሴት እንፈርድብሻለን ያሉ ሰዎች የታሉ አላት ።
፲፩ ወአውሥአት ወትቤሎ አልቦ ዘእሬኢ እግዚኦ ።

፲፩ እርሷም አለች አቤቱ የማየው የለም ። ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ አነሂ አልቦ ዘእኴንነኪ ሑሪ እትዊ በሰላም ።
እኒያ ካልፈረዱብሽ እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ አላት ። አንድም ወይቤላ ብለህ መልስ አንች ሴት ሆይ እንፈርድብሻለን ያሉ ሰዎች በምን ሀልዎት አሉ ። ትያለሽ በጽድቅን ነው በኃጢአት አላት ።
ወአውሥአት ወትቤሎ አላውቅም አለች ። አንች በሰው ካልፈረድሽእኔም አልፈድብሽም በፍቅር ሂጂ አላት ። ወእምዝ ዳግመ ኢተአብሲ ።
ሁለተኛ አትበድይ አላት ፡ ይህም አልቀረ ። ጌታ በዕለተ ዐርብ ሠለስት ሲሆን ለጸሎት ተሰውሯቸው ካታክልት ቦታ ገባ ረቂቅ መለኮት እንደሆነ ከረቂቅ መለኮት ጋር እንደ ተዋሐደ ለማጠየቅ ። እርሷ አየችው አትናገሬ ብሏት ሄደ ወዲያው መጥተው ጠየቋት የተናገርኩ እንደሆነ ይሰማኛል ብላ ባይኑዋ ጠቅሳ አሳየቻቸው ድንጊያ ሁና ቀርታለች ፡

ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ በእንተ ተፈንዎቱ መለኮታዊት ።

፲፪ ወካዕበ ነበቦሙ እግዚእ ኢየሱስ ዮሐ፥፩፥፭ ።

፲፪ ደግሞም ተናገራቸው ኢየሱስ እንዲህ ሲል አስተማራቸው ትምህርቱም ብፁዓን ነው ቢሉ ሄደው የለም ቢሉ ተመልሰው ይሰማሉ ።
አንድም ፈጽመው አልራቁምና በአጠገቡ ሁነው ይሰማሉ ትምህርቱም ሌላ ነው ያሉ እንደሆነ የተመቸ ።
ወይቤሎሙ አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ።
የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ ፤ ማለት
አንድነትን ሦስትነትን እንዲያውቅ የማደርገው እኔነኝ
ዘተለወኒ ኢየሐውር ውስተ ጽልመት ።
የተከተለኝ ማለት በኔ ያመነ ወደ ክሕደት አይሄድም ።
አላ ይረክብ ብርሃነ ሕይወት ።
የሕይወት ብርሃንን ያገኛል እንጂ በኔ አምኖ ይኖራል እንጂ ። አንድም አነ ውእቱ ብለህ መልስ ።
ሰውን ኃጢአቱን እንዲመረምር በራሱ እንዲፈርድ የማደርገው እኔ ነኝ ዘተለወኒ ፡ እኔን አብነት ያደረገ ወደ ገሃነም አይሄድም አላ ይረክብ ፡ መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል እንጂ ።

፲፫ ወይቤልዎ ፈሪሳውያን ለሊከኑ ትንዕድ ርእሰከ ።

፲፫ ፈሪሳውያንም መጽሐፍ ይወድስክ አፈ ነኪር ይላል ፡ አንተ ራስህን ታመሰግናለህን ። ኢኮነ ጽድቀ ስምዕከ ።
እንዲህስ ከሆነ ራስከን የምታመሰግን ያንተ ምስክርነትህ እውነት አይደለም ።

፲፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።

፲፬ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ እመኒ ለልየ ስምዓ ኮንኩ ለርእስየ ጽድቅ ውእቱ ስምዕየ ።
እኔ ለራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ እውነት ነው ።
እስመ አእምር እምነበ መጻእኩ ።
የመጣሁበትን አውቃለሁና ።
ወኀበሂ አሐውር ።
የምሄድበትንም አውቃለሁና ።
ወአንትሙሂ ኢትአምሩ እምኀበ መጻእኩ ወኀበሂ እኃውር ።
እናንተ ግን የመጣሁበትን የምሄድበትንም አታውቁም ።
አንትሙሰ ሕገ ዘሥጋ ትኴንኑ እናንተስ ጠበሕ ግነሰ ሠርዓ ሙሴ ከመ ትትወገር በእብን ብሏል ብላችሁ ትፈርዳላችሁ ።

፲፭ ወአንሰ ኢይኴንን ወኢመነሂ ።

፲፭ እኔ ግን በማንም በማን እንዲህ ብዬ አልፈርድም ፡

፲፮ ወእመሂ ኰነንኩ አንሰ እስመ ጽድቅ እኴንን ።

፲፮ ብፈርድም እውነት እፈርዳለሁ ተኃድገ ለከ ኃጢአትከ ኢያልኩ እፈርዳለሁ ፡ አንድም አንትሙስ እያልክ መልስ እናንተ ካነጋገር ይፈረዳል ካያያዝ ይቀደዳል ብላችሁ ትፈርዳላችሁ ፡
ወአንሰ ኢይኴንን እኔ ግን በማንም በማን አልፈርድም ወእመሂ ኰነንኩ ብፈርድም ኵላሊት ያጤ ርድም ሰውን ልብ የመረመረውን መርምሬ እፈርዳለሁ ። አንድም አንትሙስ እናንተስ ከዮሴፍ ቤት ስበላ ስጠጣ አይታችሁ እሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ ትሉ ኛላችሁ እኔ ግን የሌለኝን አምላክነት ለማንም ለማን አላስተምርም ። ወእመሂ ኰነንኩ ባስተምርም ያለኝን አምላክነት አስተምራለሁ እንጂ ። እስመ ኢኮንኩ አነ ባሕቲትየ እኔ ብቻዬን አይደለሁምና ።
አላ አነ ወአብ ዘፈነወኒ ፡
እኔ የላከኝ አብም እንጂ ።

፲፯ አኮኑ ጽሑፍ ውስተ ኦሪትክሙ ስምዓ ፪ቱ ሰብእ እሙን ውእቱ ። ዘዳ፥፲፯፥፮ ፲፱ቀር፥ ፲፭ ማቴ፥፲፰፥፲፮ ዕብ፥ ፲፥፳፰ ።

፲፯ በኦሪታችሁ ሁለት ሰዎች የመሰከሩት ምስክር እውነት ነው የሚል ጽሑፍ ያለ አይደለም ።

፲፰ ወአነሂ ስማዕት ለርእስየ ።
፲፰ እኔ ለራሴ ምስክር ነኝ ።
አብ ወስማዕትየ ዘፈነወኒ ።
የላከኝ አባቴም ምስክሬ ነው ።

፲፱ ወይቤልዎ አይቴ ውእቱ አቡከ ።
፲፱ አባትህ የት አለ አሉት ።
ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ኢኪየየ ተአምሩ ።
እኔንም አታውቁ ።
ወኢአቡየ ።
አባቴንም አታውቁም አንድም እኔን ሳታውቁ አባቴን አታውቁ አላቸው ።
ሶበሰ ኪያየ አእመርክሙ አምአእመርክምዎ ለአቡየኒ ።
እኔንስ ዐውቃችሁኝ ቢሆን አባቴንም ባወቃችሁት ነበር ።

፳ ወዘንተ ነገረ ተናገሮሙ እግዚእ ኢየሱስ በኀበ ሙዳየ ምጽዋት እንዘ ይሜህሮሙ ።

፳ በምኲራብ ሲያስተምራቸው መባውን የሚያኖሩበት ሣጥን ካለበት ቦታ ይኸንን ነገራቸው። እስራኤል ከቤተ እግዚአብሔር እጅ ሳይነሱ አይውሉም ባዶ እጃቸውንም አይሄዱም ድቀት ያገኘው አንዱን ቅጽር ገብቶ ከዚያ ትቶ ይሄዳል ድቀት ያላገኘው ከውስጥ ገብቶ ሰጥቶ ይሄዳል ካህናት እያነሱ የሚያበላሹት ሆነ፤ንጉሡ ኢዮአስ ሊቀ ካህናቱ ዮዳሄ ይባላሉ መክረው ብር የሚያስገባ እጅ የማያስገባ ሣጥን አኖሩ ሲመላ ዕቃቤት እያገቡ ያኖሩታል ሁለት ሦስት ሁነው እንሥተው እንዳይወስዱት ጠባቂም አለው ይህ ባለበት ።
ወኢአኃዝዎ ።
አልያዙትም እስመ ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜሁ ።
የሚያዝበት ጊዜ ገና አልደረሰምና ።

፳፩ ወካዕበ ይቤልዎ እግዚእ ኢየሱስ
አንሰ አሐውር ።

፳፩ ጌታም ደግሞ እሄዳለሁ አላቸው ።
ተኃሥሡኒ ። ትሹኛላችሁ ።
ወኢትረክቡኒ ። አታገኙኝም ።
ወትመውቱ በኃጢአትክሙ ።
በኃጢአታችሁም ትሞታላችሁ ።
ወኀበ አነ አሐውር አንትሙ ኢትክሉ መጺአ
እኔ ወደምሄድበት መምጣት አይቻላችሁም ።
ወትመውቱ በኃጢአትክሙ ።
በኃጢአታችሁ ሳላችሁ በኃጢአታችሁ ፍዳ ተፈርዶባችሁ በነፍስ ትሞታላችሁ

፳፪ ወይቤሉ አይሁድ ይቀትልኑ እንጋ ርእሶ ለሊሁ ዘይብለነ ኀበ አነ አሐውር አንትሙ ኢትክሉ መጺአ ፤

፳፪ አይሁድም እኔ ወደምሄድበት እናንተ መምጣት አይቻላችሁም የሚለን ታንቆን ይሞታል አሉ ።

፳፫ ወይቤሎሙ አንትሙሰ እምታሕቱ አንትሙ ።

፳፫ እናንተስ በግብርም በባሕርይም ባናኑቋርም ከዚህ ዓለም የተገኛችሁ ናችሁ ፤
ወአንሰ እምላዕሉ አነ ፤
እኔ ግን ባናኑዋርም በባሕርይም ከሰማይ የተገኘሁ ነኝ ።
አንትሙሰ እምዝንቱ ዓለም አንትሙ ።
እናንተስ ባናኑዋርም በባሕርይም ከዚህ ዓለም የተገኛችሁ ናችሁ ።
ወአንሰ ኢኮንኩ እም ዝንቱ ዓለም ።
እኔ ግን ከዚህ ዓለም አይደለሁም ።

፳፬ ወናሁ እቤለክሙ ከመ ትመውቱ በኃጢአትክሙ

፳፬ በኃጢአት ሳላችሁ ንስሐ ሳትገቡ ፤አንድም በኃጢአታችሁ በመጣ ፍዳ በነፍስ እንድትሞቱ እነሆ ነግሬያችኋለሁ ለእመ ኢአመንክሙ ከመ አነ ውእቱ ትመውቱ በኃጢአትክሙ ፤
እኔ እንደሆንኩ ባታምኑ ማለት የባሕርይ አምላክ እንደሆንኩ ካላመናችሁ በኃጢአት ትሞታላችሁ ።

፳፭ ወይቤልዎ አንተ መኑ አንተ
፳፭ አንተ ማነህ አሉት ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ቀዳሚኒ ነገርኩክሙ ።
ጌታም ቀድሞ ነግሬያችሁ ነበር ።

፳፮ ወብዙኀ ብየ ዘእብል በእንቲአክሙ ።
፳፮ ለናንተም የምነግራችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ።
ወእኴንን ቦቱ ።
ኪያሁ ሲል ነው ያኑ የማስተምረው ።
ወባሕቱ ዘፈነወኒ ጻድቅ ውእቱ ።
ነገር ግን የላከኝ አባቴ የባሕርይ አምላክ ነው ።
ወአንሰ ዘሰማዕኩ በኀቤሁ እነግር ለዓለም ።
እኔም በርሱ በሀልወና የሰማሁትን ለዓለም አስተምራለሁ ።

፳፯ ወኢያእመሩ ከመ በእንተ አብ ይቤሎሙ።
፳፯ ጻድቅ ውእቱ ያለው ስለ አብ እንደሆነ አላወቁም ።

፳፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አመ ተለዓለ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ይእተ አሚረ ተአምሩ ከመ አነ ውእቱ ።

፳፰ የሰው ልጅ ክርስቶስ ከፍ ባለ ጊዜ ማለት በተሰቀልኩ ጊዜ የባሕርይ አምላክ እንደሆንኩ ታውቃላችሁ ።
ወአኮ ዘእምኅቤየ ዘእነግር ።
የማስተምረውም ከራቤ አንቅቼ እንዳይደለ ።
አላ በከመ መሐረኒ አቡየ ከማሁ እነግር ።
አባቴ በህልውና የነገረን እንደነገረኝ አስተምራለሁ እንጂ ።

፳፱ ወዘፈነወኒ ሀሎ ምስሌየ ።
፳፱ የላከኝ አባቴ በኔ ህልው ነው ።
ወኢየኃድገኒ አብ ባሕቲትየ ።
አብ ብቻየን አይተወኝም ማለት አይለየኝም ።
እስመ አነ እገብር ሥምረቶ ዘልፈ በኵሉ ጊዜ ።
በፈቃድ አንድ ነንና ። አንድም ዘወትር ፈቃዱን እፈጽማለሁና ።

፴ ወዘንተ ብሂሎ ብዙኃን እለ አምኑ ቦቱ ።
፴ ይህን በተናገረ ጊዜ ብዙ ሰዎች አመኑበት ያመኑበት ብዙ ሰዎች ናቸው ።

፴፩ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለእለ የአምኑ ቦቱ አይሁድ አንትሙሂ ለእመ ነበርክሙ በቃልየ አማን አርዳእየ አንትሙ ።

፴፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑበትን አይሁድን እናንተም ባስተማርኋችሁ ትምህርት ብትጸኑ በውነት የኔ ደቀመዛሙርት ናችሁ አላቸው ።

፴፪ ወተአምርዋ ለጽድቅ ።
ጽድቅንም ታውቋታላችሁ ።
ወጽድቅኒ ታግዕዘክሙ ።
ጽድቅም ነጻ ታወጣችኋለች ።

ዘከመ ገሠጸ ኢየሱስ ትዝኅርቶሙ ለአይሁድ ።

፴፫ ወአውሥኡ አይሁድ ወይቤልዎ ዘርዓ አብርሃም ንሕነ ።

፴፫ እኛስ የአብርሃም ልጆች ነን ።
ወእም አመኮነ ኢተቀነይነ ግሙራ ወኢለመኑሂ ።
ከሆነ ጀምሮ ለማንም ለማን ተገዝተን አናውቅም ።
እፎ እንከ ትብለነ አንተ ትግዕዙ ።
እንደምን አንተ አርነት ትወጣላችሁ ትለናለህ አሉት ይኸም ሐሰታቸው ነው ። በግብጽ ሁለት መቶ ዐሥራ አምስት ። በባቢሎን ሰባ ዘመን ተገዝተዋል ።

፴፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ። ሮሜ፡፮፡ ፲፰ ፪ ጴጥ፡፪፡ ፲፱ ።

፴፬ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ አማን አማን እብለክሙ ኵሉ ዘይገብራ ለኃጢአት ገብራ ውእቱ ለኃጢአት ።
ኃጢአት የሚሠራ ሁሉ የኃጢአት ተገዥ ነው ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፴፭ ወገብርሰ ኢይነብር ውስተ ቤት ለዝሉፉ
፴፭ የኃጢአት ተገዥ ማለት ኃጥእ በመንግሥተ ሰማይ አይኖርም ። ወወልድሰ ይነብር ለዓለም ። ምእመን ግን በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል ። ፩ም ወገብርሰ እያልክ መልስ ። ገብር ሙቤ በምእመን አድሮ አይመግብም ። ወወልድሰ እኔ ግን አድሬ እመግባለሁ ። አንድም ባሪያ በጌታው ቤት አይኖርም ይሸጠው ይለውጠው ማጫ ጥሎት አሳልፎ ይሰጠውም እንደሆነ አያውቅምና ። ወወልድሰ ልጅ ግን ለዘለዓለም በቤት ይኖራል ይህ ሁሉ የለበትምና ።

፴፮ ወእም ከመስ ወልድ አግዐዘክሙ አማን ግዑዛን አንትሙ ።

፴፮ እኔ ነጻ ካወጣኋችሁ በውነት ነጻ ናችሁ ።
፴፯ ወአእምር ከመ ዘርዓ አብርሃም አንትሙ ።
፴፯ የአብርሃም ልጆች ነን እንድትሉስ አውቃለሁ ።
ወባሕቱ ተሐሥሡ ትቅትሉኒ ።
የአብርሃም ልጅ ባትሆኑ ልትገሉኝ ትሻላችሁ እንጂ ።
እስመ ኢይነብር ቃልየ ኀቤክሙ ።
ትምህርቴን አትቀበሉኝምና ።

፴፰ ወአንሰ ዘርኢኩ በኀበ አቡየ እነግር ።
፴፰ እኔ ካባቴ በህልውና ያየሁትን አስተምራለሁ ።
ወአንትሙሰ ዘርኢክሙ በኀበ አቡክሙ ትገብሩ ።
እናንተ ግን ካባታችሁ ከሰይጣን የሰማችሁትን ትሠራላችሁ ።

፴፱ ወአውሥኡ ወይቤልዎ ለነሰ አብርሃም አቡነ ።

፴፱ እኛስ የአብርሃም ልጆች ነን አሉት ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ሶበሰ ውሉደ አብርሃም አንትሙ ግብረ አብርሃም እምገበርክሙ ።
የአብርሃም ልጆችስ ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ በሠራችሁ ነበር አላቸው ።
ወቃሎሂ እምዓቀብክሙ ወኪያየሂ እምአፍቀርክሙኒ ።
ሕጉን በጠበቃችሁ እኔንም በወደዳችሁ ነበር ።

፵ ወይእዜሰ ተኃሥሡ ትቅትሉኒ ብእሴ ጻድቀ ዘጽድቀ እነግረክሙ ዘሰማዕኩ በኀበ እግዚአብሔር ።

፵ ነገር ግን ዛሬ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሰማሁትን እውነተኛ ትምህርት የማስተምራችሁን እውነተኛ መምህር እኔን ልትገሉኝ ትሻላችሁ ።
ወአብርሃምስ ኢገብረ ከመዝ ።
አብርሃምስ እንዲህ ያለ ሥራ አልሠራም ፤ አስተምረው አላምንም ማለቱ ይቅርና ያስተማረው ሳይኖር በአእምሮ ጠባይዕ ዐውቆ በሥነ ፍጥረት ተመራምሮ አመነ እንጂ ። አንድም አብርሃምስ እንዲህ አላደረገም ሰው ልግደል ማለቱስ ቀርቶ ከተመሳቀለ መንገድ አራት ደጅ ያላት ቤት ሠርቶ የቲራበ እያበላ የተጠማ እያጠጣ የታረዘ እያለበሰ ነፍስ ያድን ነበር እንጂ ።

፵፩ አንትሙሰ ትገብሩ ግብረ አቡክሙ ።
፵፩ እናንተስ ያባታችሁን የሰይጣንን ሥራ ትሠራላችሁ ።
ወይቤልዎ ንሕነሰ ኢተወለድነ እምዝሙት ።
እኛስ ከሰይጣንም አልተወለድንም ።
አላ አሐዱ አብ ብነ ።
ከአብርሃም ተወልደናል እንጂ አንድ አባት አለን እንጂ ።
ወውእቱ እግዚአብሔር ።
ያውም እግዚአብሔር ነው ።
አንድም አብርሃም በአምልኮተ ጣዖት ሳለ የወለደው ልጅ ኑሮት ከርሱ አልተወለድንም አለ አሐዱ አብ ብነ ። በአምልኮተ እግዚአብሔር ሳለ ከወለደው ከይስሐቅ ተወልደናልና አንድ አባት አለን ያውም እግዚአብሔር ነው እንጂ ። አንድም ንሕነሰ ኢተወለድነ ፤ በሴሰኝነት ከተወለደው ከኤስማኤል አልተወለድንም በሩካቤ ዘበሕግ ከተወለደው ከይስሐቅ ተወልደናልና አንድ አባት አለን እንጂ ያውም እግዚአብሔር ነው ።

፵፪ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ሶበሰ እግዚአብሔር አቡክሙ እምአፍቀርክሙኒ ኪያየ ።

፵፪ እግዚአብሔርስ አባታችሁ ቢሆን እኔን በወደዳችሁኝ ነበር ።
ወቃልየኒ እምዓቀብክሙ ።
ሕጌንም በጠበቃችሁ ነበር ።
እስመ አነ እምኀበ እግዚአብሔር ወፃእኩ ወመጻእኩ ።
እኔ ከእግዚአብሔር አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልጄ መጥቻለሁና ።
ወአኮ ለልየ ዘመጻእኩ ።
በኔ ፈቃድ ብቻ ሰው አልሆንኩም ።
አላ ውእቱ ዘፈነወኒ ።
በላከኝ ባባቴም ፈቃድ ነው እንጂ ።

፵፫ እፎ እንከ ተአምኑ ቃልየ ።
፵፫ በኔ ማመን እንደ ምን ይቻላችኋል ።

እስመ ትክሉ ሰሚዓ ነገረ ዚአየ ።
ትምህርቴን አትቀበሉኝምና ።

፵፬ አንትሙሰ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ፣ ፩ ዮሐ፫ ፡ ፰ ።

፵፬ እናንተስ ካባታችሁ ከሰይጣን ወገን ናችሁ።
ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትፈቅዱ ትግበሩ ።
ያባታችሁ የሰይጣንን ፈቃድ ልትሠሩ ትወዳላችሁ ።
ወውእቱ ቀታሌ ነፍስ ስብእ ውእቱ እምጥንቱ ።
እርሱ ከጥንት ጀምሮ ነፍሰ ገዳይ ነው ፤ በቃየል አድሮ አቤልን ሲያስገድል ማን ነገረው ።
ወኢይቀውም በጽድቅ ።
በውነት ጸንቶ አይኖርም ፤ እምላክነትን ሲሻ ማን አስተማረው ።
እስመ አልቦ ጽድቅ በኀቤሁ ።
በርሱ ዘንድ እውነት የለምና ።
ወሶበሂ ይነብብ ሐሰተ እምዚአሁ ይነብብ ።
ሐሰትን በተናገረ ጊዜ ከራሱ አንቅቶ ይናገራል ።
አንድም በተናገረ ጊዜ ሐሰትን ከራሱ አንቅቶ ይናገራል ።
እስመ ሐሳዊ ውእቱ ።
ሐሰተኛ ነውና ።
ወአቡሃ ለሐሰት ።
የሐሰት ነቋ መገኛዋ ነውና ዓመፃ ወዕአት እመዛግብቲሃ እንዲል ።

፵፭ ወአንሰ እስመ ጽድቀ እነግር ወኢተአምኑኒ ።

፵፭ እኔ እውነት ባስተምር አትቀበሉኝም ፤ መኑ ማንሻ ። አንድም እኔ እውነት ባስተምር ባትቀበሉኝ ።

፵፮ መኑ እምኔክሙ ዘይዛለፈኒ በእንተ ኃጢአት ።

፵፮ ከእናንተ ወገን ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማለት ኃጢአት ሠርተሃል ብለው አልሠራሁም የሚለኝ ማነው ። አንድም ኃጥእ ነህ ብለው መልሶ ኃጥእ ነህ የሚለኝ ማነው ። በገቢርም እንዳልሠራ ለማጠየቅ እንዲህ አለ ። በነቢብም እንዳልሠራ ለማጠየቅ ነቢይ ኢገብረ ኃጢአተ ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ ብሎ መስክሮለታል በሐልዮም እንዳልሠራ ለማጠየቅ ይመጽእ መልአኩ ለዝንቱ ዓለም ወኢይረክብ በላዕሌየ ወኢምንተኒ ብሏል ። ፍጹማን ነን በሚሉ ሰዎች ዘለፋ ሊሆንባቸው እንዲህ አለ ።

ወእመሰ አነ ጽድቀ እነግር ለምንት ኢተአምኑኒ ።
እኔ እውነት የማስተምር ከሆነ የማትቀበሉኝስ ለምን ነው ።

፵፯ ዘሰ እምእግዚአብሔር ውእቱ ቃለ እግዚአብሔር ይሰምዕ ።

፵፯ ከእግዚአብሔር የተገኘ የእግዚአብሔር ወገን የእግዚአብሔርን ነገር ይሰማል ይቀበላልም ።
ወበእንተ ዝንቱ አንትሙሰ ኢትሰምዑኒ እስመ ኢኮንክሙ እምእግዚአብሔር ።
እናንተ ግን የእግዚአብሔር ወገን አይደላችሁምና ስለዚህ አትቀበሉኝም ።

፵፰ ወተሰጥውዎ አይሁድ ።
፵፰ አይሁድም መለሱለት ።
ወይቤልዎ አኮኑ ሠናየ ንቤለከ ከመ ሳምራዊ አንተ ፤
ሳምራዊ እንደሆንክ ።
ወጋኔን ብከ ።
ሎቱ ስብሐት ፤ ጋኔን አድሮብህ እንዳለ በውነት ነግረንህ የለምን አሉት ። ሳምራዊ ያይወልደው ያዕቆብን ያዕቆብ አቡነ እንዲል ፤ አንተም ያይወልድህ እግዚአብሔርን አባቴ ትላለህ ለማለት ።

፵፱ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ አንሰ ጋኔን አልብየ ፤

፵፱ ጌታም መለሰ ሳምራዊ ላሉት አይመልስላቸውም በስመ ትዕይርቱ ተጠቅመንበታልና ፤ እኔስ ጋኔን የለብኝም አላቸው ።
ወባሕቱ አከብር አባየ ፤
ነገር ግን አባቴን አከብራለሁ ፤
አከብር ።
አከብር ዘንድ ነው እንጂ ፤
ወአንትሙሰ ታስተሐቅሩኒ ።
ትንቁኛላችሁ ማለት እናንተ ግን ዕሩቅ ብእሲ ትሉኛላችሁ ።

፶ አንሰ ኢየኃሥሥ ተድላ ለርእስየ ።

፶ እኔ ራሴን ደስላለኝ አልሻም ማለት የሌለኝን እምላክነት እምላክ ነኝ ብዬ አላስተምርም።
ሀሎ ዘየኃሥሥ ሊተ ፤
የሚመሰክርልኝ አባቴ አለ ።
ወዘሂ ይኴንን ።
የሚያስተምርልኝ፥ አንድም ባታምኑ የሚፈርድልኝ።

፶፩ አማን አማን እብለክሙ ዘዓቀበ ቃልየ ኢይጥዕሞ ለሞት ለዓለም ።

፶፩ ሕጌን የጠበቀ ለዘለዓለም ሞት የለበትም ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ በሥጋ ቢሞት በነፍስ አይሞትም ፈርሶ በስብሶ አይቀርም ትንሣኤ ዘለክብር ይነሣል ።

፶፪ ወይቤልዎ አይሁድ ይእዜሰኬ አእመርናከ ከመ ጋኔን ብከ ።

፶፪ ሎቱ ስብሐት ፤ ጋኔን አድሮብህ እንዳለ ገና ዛሬ ዐወቅን ።
አብርሃም ጥቀ ሞተ ።
አብርሃም ስንኳ ሞተ
ወነቢያትኒ ሞቱ ፤
ነቢያትም ሞቱ ።
ወአንተሰ ትብል ዘዓቀበ ቃልየ ኢይጥዕሞ ለሞት ለዓለም ።
አንተ ግን ሕጌን የጠበቀ ሞት የለበትም ትላለህ ።

፶፫ አንተኑ ተዓቢ እምአብርሃም አቡነ ዘሞተ ።
፶፫ ከሞተ አባታችን ከአብርሃም አንተ ትበልጣለህን ።
ወእምነቢያትኒ እለ ሞቱ ።
ከሞቱ ከነቢያት ትበልጣለህን ፤
መነ ትረሲ ርእሰከ ።
ማንኝ ትላለህ መጽላት ምቀኝነት ፈራሽ ነገር አናገራቸው ለልማዱ ጠባቂውን ከጠባቂ አስጠባቂውን ካስጠባቂ አነጻጽሮ መናገር ይገባ ነበር እርሳቸው ግን አስጠባቂውን ከጠባቆች አነጻጽረው ተናገሩ ።

፶፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፶፬ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ እመሰ ለልየ ሰባሕኩ ርእሰየ ኢይበቍዓኒ ስብሐትየ ወኢምንተኒ ።
እኔ ራሴን ባከብር ምስጋናዬ አይረባኝም አይጠቅመኝም ።
ሀሎ አቡየ ዘይሴብሐኒ ።
የሚያከብረኝ አባቴ አለ ፤ አንድም እኔ ራሴን ባመሰግን ምስጋናዬ ባይረባኝ ባይጠቅመኝ የሚያከብረኝ አባቴ አለ ።
ዘአንትሙ ትብልዎ አምላክነ ውእቱ ።
እናንተ አምላካችን የምትሉት ፤

፶፭ ወኢተአምርዎ
፶፭ የማታውቁት ፤

ወአንሰ አአምሮ ፤
እኔ ግን አውቀዋለሁ ።
ወእመሰ እቤ ኢየአምሮ እከውን ከማከሙ ሐሳዌ
ወአንሰ አአምሮሂ ።
እኔ ግን አውቀዋለሁ አላውቀውም ብል እንደናንተ ሐሰተኛ ሆንኩ ።
ወቃሎሂ አዓቅብ ።
ሕጉንም እጠብቃለሁ ፤

፶፮ አብርሃም አቡክሙ ተመነየ ከመ ይርአይ ዕለትየ ።
አንተኑ ተዓቢ እምአብርሃም ።

፶፮ አሁን ብለውት ነበርና ፤ አባታችሁ አብርሃም የምወለድበትን ቀን ሊያይ ተመኘ ። ተነበየ ጸለየ ፈተወ ይሳል ወደደ አመለከተ በል ።
ወርእየ ወተፈሥሐ ።
አይቶም ደስ አለው ።

፶፯ ወይቤልዎ አይሁድ ኀምሳ ዓመት አልብከ በእፎ አብርሃምሃ ርኢከ ፤

፶፯ ኀምሳ ዓመት ያልሞላህ አብርሃምን እንደምን አየህ አሉት ። ምን ይዘው እንዲህ አሉት ቢሉ በሃያ ዓመት ደግ ሹመት ይሾማሉ ሃያ አምስት ዓመት አገልግለው ዝቅ ያለ ሹመት ይሾማሉና ።

፶፰ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አማን አማን እብለከሙ እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ ።

፶፰ አብርሃም ሳይፈጠር ነበርኩ ብዬ እንደ ነበርኩ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ፤
አሪት ዘልደት እንዲል ፤ ከአብርሃም አስቀድሞ ታራስ አልነበረምን ቢሉ በአብርሃም መላውን መናገር ነው

፶፱ ወነሥኡ አይሁድ እብነ ከመ ይውግርዎ ።
፶፱ ሊጣሉት አይሁድ ደንጊያ አነሱ ። ብእሴ ጻድቅ ያሰው ማኅደር ፤ እምቅድመ ይትወለድ ያለውን ኅዳሪ ነው ይላል ፈረንጅ ነሥኡ እብነ ከመ ይውግርዎ ባለው ይረታል ።
ወተኀብአሙ እግዚእ ኢየሱስ ወወፅአ እምኵራብ ወኀለፈ እንተ ማእከሎሙ ።
ከምኵራብ ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ ፤ ረቂቅ መለኮት እንደሆነ ከረቂቅ መለኮት ጋራ እንደ ተዋሐደ ለማጠየቅ ።

ዘከመ ፈወሶ ለዘዕውሩ ተወልደ ።
ምዕራፍ ፱ ።

፩ ወእንዘ የኀልፍ እምህየ ርእየ ብእሴ ዘዕውሩ ተወልደ እምከርሠ እሙ ።

፩ እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ ብሎ ነበርና ።
እስመ ስምዓ ቃላቲሁ ምግባሩ ውእቱ እንዲል ነገሩን በሥራው ለማስረዳት ያመጣዋል ከዚያ አልፎ ሲሄድ ከናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ሁኖ የተወለደ ሰው አገኘ ። ዕውር ሁኖ ተወልዷል ቢሉ የተመቸ አንድም ልሙጽ ሁኖ ተወልዷል ።

፪ ወተስእልዎ አርዳኢሁ ወይቤልዎ ረቢ በኃጢአተ መኑ ተወልደ ዝንቱ ዕውር ።

፪ መምህር ሆይ ይህ ሰው ዕውር ሁኖ የተወለደ በማን ዕዳ ነው ብለው ደቀ መዛሙርቱ ጠየቁት። በዘርእሱኑ ፤ በራሱ ዕዳ ነውን ፤ ተነክሩ ኃጥአን እማኅፀን ያለውን ይዘው ።
ወሚመ በዘአዝማዲሁ ። ወይም ባባት በናቱ ዕዳ ነውን ዕውር ሆኖ ይወለድ ዘንድ ። ሕፃናተ አብዕልት ይመውቱ በጌጋየ ወሳድያኒሆሙ ያለውን ይዘው ፤

፫ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢውእቱ አበሰ ።

፫ በርሱም ዕዳ አይደል ። ወኢአዝማዲሁ ባባት በናቱም ዕዳ አይደል ።
ዳዕሙ ከመ ያስተርኢ ግብረ እግዚአብሔርበላዕሌሁ። የእግዚአብሔር ሥራ በርሱ ይገለጥበት ዘንድ ነው እንጂ ማለት አምጺኦ ዓለማትንቱ ከሃሊነቱ ጌትነቱ ተአምራቱ መግቦቱ ዓይን ነሥቶ ዓይን ለሌለው ዓይን ሰጥቶ መመገቡ ይታወቅ ዘንድ ነው እንጂ አላቸው ።

፬ ወባሕቱ ርቱዕ ሊተ እግበር ግብሮ ለዘፈነወኒ እንዘ መዓልት ውእቱ ።

፬ ነገር ግን መዓልት ዕድሜየ ሳለ ያባቴን ሥራ ሠርቼ እናንተን ማሳመን ይገባኛል ።
እስመ ትመጽእ ሌሊት ዘኢይክል ቦቱ አሐዱሂ ገቢረ። አንዱ ስንኳ ሥራ ሊሠራበት የማይችልበት ሞት አለብኝና ከፍዳ የነጻንበትን ልጅነት ያገኘንበትን ሞቴን ስለምን በሌሊት መሰለው ቢሉ ሰው በመዓልት የሚሠራውን በሌሊት እንዳይሠራው እርሱም በሕይወተ ሥጋ ሳለ የሚሠራውን ከሞተ በኋላ አይሠራውምና አንድም ፤
ዘኢትክሉ ቦቱ ገቢረ አሐዱሂ እምዘ ሀሎ ውስተ ዓለም ።
በዚህ ዓለም ካለው ሥራ አንዱን ስንኳ ልትሠሩበት የማትችሉበት ሞት አለባችሁና መዓልት ዕድሜያችሁ ሳለ ያባቴን ሥራ ሠርቼ እናንተን ማሳመን ይገባኛል።

፭ እንዘ ሀሎኩ ውስተ ዓለም አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ።

፭ በዚህ ዓለም ሣለሁ የሰው ዕውቀቱ እኔ ነኝ።
፮ ወዘንተ ብሂሎ ወረቀ ውስተ ምድር ።
፮ ይኸን ተናግሮ ምራቁን ትፍ አለ ።
ወገብረ ጽቡረ በምራቁ ።
በምራቁም ጭቃን ለወሰ ።
ወቀብዖ አዕይንቲሁ ለውእቱ ዕውር ።
የዚያን ዕውር ዓይኑን ቀባው ።

፯ ወይቤሎ ሑር ተሐፀብ በምጥማቃተ ሰሊሆም ።

፯ ሂደህ በፈሳሽ ውኃ ተጠመቅ አለው ።
ዘበትርጓሜሁ ሐዋርያ ።
ፈላሽ ማለት ነው ፤ ሑር ማለቱ አራቱ ባሕርያት እንዲተካከሉለት ሥስቱ ከዚህ እሉ ነፋስ ሲሄድና ሲመለስ እንዲተካከልለት ። እንድም እየተመራ ሂዶ እያየ ቢመለስ ተአምራቱ ድንቅ ይባላልና

ወሖረ ወተሐፀበ ።
ሂዶ ተጠመቀ ።
ወገብአ እንዘ ይሬኢ ።
እያየ ተመለሰ ።

፰ ወአግዋሪሁሰ ወእለሂ የአምርዎ ትካት
ወይሬእይዎ እንዘ ይስእል ይቤሉ ።

፰ ጐረቤቶቹ ቀድሞ ሲለምን እንደነበረ የሚያውቁት ዕውር እንደሆነ ።
አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ዘይነብር ውስተ ፍኖት ወይስእል
ይህ በመንገድ ተቀምጦ ይለምን የነበረው አይደለምን አሉ ።

፱ ወቦ እለ ይቤሉ ውእቱ ዝንቱ ፤
፱ ነው ያሉም አሉ ።
ወካልዓን ይቤሉ አልቦ ።
ሌሎቹም እርሱ አይደለም ፤
አላ ይመስሎ ፤
ይመስለዋል እንጂ አሉ ፤
ወለሊሁሰ ይቤ አነ ውእቱ ።
እርሱ ግን እኔ ነኝ አለ ።

፲ ወይቤልዎ እፎ ተከሥታ አዕይንቲከ ።
፲ ዓይንህ እንደምን በራልህ አሉት ።

፲፩ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ብእሲሁ ዘስሙ
ኢየሱስ ጽቡረ ገብረ በምራቁ ወቀብዓኒ አዕይንትየ።
ኢየሱስ የሚባል ሰው በምራቁ ጭቃ ለውሶ ዓይኔን
ቀባኝ ።
ወይቤለኒ ሑር ተሐፀብ በምጥምቃት ሰሊሆም ።
ሂደህ በፈሳሽ ውኃ ተጠመቅ አለኝ ።
ወሖርኩ ወተሐፀብኩ ፤
ሄጄ ተጠመቅሁ ፤
ወርኢኩ ፤ አየሁ አላቸው ።

፲፪ ወይቤልዎ አይሁድ አይቴ ውእቱ ብእሲሁ
፲፪ ያሰው የት አለ አሉት ።
ወይቤሎሙ ኢየአምር ።
አላውቅም አላቸው ።

፲፫ ወወሰድዎ ኀበ ፈሪሳውያን ለውእቱ ዘዕውሩ ተወልደ ።

፲፫ ለኛ ባትነግረን አለቆች በጢጢ
በሳንባ ጠለፍ ገርፈው ያናግሩሃ የለምን ብለው
ወደ ፈሪሳውያን ይዘውት ሄዱ ።

፲፬ እስመ ሰንበት አሜሁ አመ ገብረ እግዚእ
ኢየሱስ ጽቡረ በምራቁ ወከሠቶ አዕይንቲሁ ።

፲፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምራቁ ጭቃ
ለውሶ ዓይኑን ያዳነበት ቀኑ ቅዳሜ ነበርና ። ወሰንበት አሜሁ ቀኑ ቅዳሜ ነበር ።

፲፭ ወተስእልዎ ካዕበ ፈሪሳውያን ዘከመ እፎ
ርእየ ።

፲፭ ለብላቴኖቻቸው ካዕበ አለ ። አንድም
እንደ ዳነ ፈሪሳውያን ሁለተኛ ጠየቁት ።
ወይቤልዎ እፎ ርኢከ ።
እንደምን ዳንህ አሉት ።
ወይቤሎሙ ጽቡረ ገብረ በምራቁ ወወደየ ውስተ
አዕይንትየ ።
በምራቁ ጭቃ ለውሶ ካይኔ አገባልኝ ።
ወሖርኩ ወተሐፀብኩ ወርኢኩ ።
ሔጄ ተጠምቄ ዳንኩ አላቸው ። ቢጋሩ ያለ ነው
ቢሉ እንደእንዝርት ራስ ቀርጾ ያገባለታል ይህስ
እንዳይሆን አዳም በዙር ያልሆነበት ሥጋ አይፈጥርም
ብሎ እንደ ሥዕል ሣይ ይነድፍለታል ፤ ጽጌያት
ከአዕጹቃቸው እንዲፈነዱ ከባሕርዩ ያነቃለታል።

፲፮ ወቦ እለ ይቤሉ እምፈሪሳውያን ።
ዝንቱ ብእሲ ኢኮነ እምእግዚአብሔር ዘኢየዓቅብ
ሰንበተ ።

፲፮ ከፈሪሳውያን ወገን የሚሆኑ ሰዎች ቅዳሜን የማያከብር ይህ ሰው ደግም አይደለም ያሉም
አሉ ።
ወቦ እለ ይቤሉ በአይቴ ይክል ብእሲ ኃጥእ ገቢረ
ዘከመዝ ተአምረ ።
ኃጥእ ሰው በደረቅ ግንባር ዓይን መፍጠር እንደምን
ይቻለዋል ያሉም አሉ ።
ወተናፈቁ በበይናቲሆሙ በእንተ ዝንቱ ነገር ።
ኃጥእ ነው አይደለም በማለት እርስ በርሳቸው ጸብ
ሆነ ተለያዩ ።

፲፯ ወይቤልዎ ካዕበ ለውእቱ ዕውር ምንተ
ትብል አንተ በእንቲአሁ እስመ ከሠተከ አዕይንቲከ።

፲፯ ሁለተኛ ያነን ዕውር ዓይንህን አብርቶል
ሃልና አንተ የርሱን ነገር ምን ትፈርዳለህ አሉት ።
ወይቤሎሙ ነቢይ ውእቱ ፤
እርሱም መለሰ ዓለም ። ነቢየ ያነሥእ ለክሙ ተብሎ
የተነገረለት ነቢይ ነው ።

፲፰ ወኢአምንዎ አይሁድ ከመ ዕውሩ ተወልደ ወርእየ ።

፲፰ ዕውር ሁኖ ተወልዶ ኋላ እንደዳነ አይሁድ አላመኑም ።

፲፱ እስከ ጸውዑ አዝማዲሁ ለዘርእየ ።
ዘመዶቹን ጠርተው እስቲጠይቁ ድረስ ።
ወተስእልዎሙ ወይቤልዎሙ ዝኑ ውእቱ ወልድ
ክሙ ዘትብሉ ዕውሩ ተወልደ ።

፲፱ ጠየቋቸውም እንዲህ ሲሉ ዕውር ሁኖ
የተወለደ የምትሉት ይህ ልጃችሁ ነውን ።
ወበእፎ እንከ ይእዜ ይሬኢ ።

ዛሬስ እንደምን ዳነ ብለው ጠየቋቸው ።

፳ ወአውሥኡ አዝማዲሁ ።
፳ እናት አባቱም መለሱ ።
ወይቤሉ ነአምር ከመ ዝንቱ ውእቱ ወልድነ ።
ልጃችን ይህ እንደሆነ ።
ወከመሂ ዕውሩ ተወልደ ።
ዕውር ሁኖም እንደተወለደ እናውቃለን አሉ ።

፳፩ ወይእዜሰ ዘከመ እፎ ይሬኢ ።
፳፩ ዛሬ ግን እንደምን እንደዳነ ።
አው መኑ ከሠቶ አዕይንቲሁ ኢነአምር ።
ማንም ዓይኑን እንዳዳነው አናውቅም ።
ኪያሁ ተስአልዎ ።
እርሱን ጠይቁት ።
እስመ ልሂቅ ውእቱ ።
ዐዋቂ ነውና ።

ወይክል ተናግሮ ለርእሱ ።
ለመናገር በቅቷል ፤

፳፪ ወዘንተ ይቤሉ አዝማዲሁ እስመ ይፈርህዎሙ ለአይሁድ ።

፳፪ አባት እናቱ አይሁድን ስለ ፈሩ ይህን ተናገሩ ።
እስመ አዘዙ አይሁድ ለእመ ቦ ዘአምነ ቦቱ ከመ ውእቱ ክርስቶስ ይሰደድ እምኵራብ ክርስቶስ እንደሆነ ያመነበት ሰው ቢኖር ከምኵራብ ይለይ ብለው ዐዋጅ ነግረው ነበርና ።

፳፫ ወበእንተ ዝንቱ ይቤሉ አዝማዲሁ ልሒቅ ውእቱ ሎቱ ተስአልዎ ።

፳፫ ስለዚህ አባት እናቱ ዐዋቂ ነው ለመናገር በቅቷል እርሱን ጠይቁት አሉ ።

፳፬ ወጸውዕዎ ዳግመ ለውእቱ ብእሲ ዕውር ።
፳፬ ሁለተኛም ያንን ዕውር የነበረውን ሰው ጠሩት ።
ሑር ሀብ ስብሐተ ለእግዚአብሔር ።
ይህ ሰው አላዳነህም እግዚአብሔር ነውና ያዳነህ ሄደህ እግዚአብሔርን አመስግን ።
ንሕነሰ ነአምር ከመ ኃጥእ ውእቱ ዝብእሲ ።
ይህ ሰው ግን ኃጥእ እንደሆነ እኛ እናውቃለን ።

፳፭ ወአውሥአ ውእቱ ብእሲ ዕውር ።
፳፭ ያም ሰው መለሰ ።
ወይቤሎሙ አንሰ ኢየአምር ከመ ኃጥእ ውእቱ ።
እኔ ኃጥእ መሆኑን አላውቅም ።
ወዘንተ ባሕቱ አአምር ከመ ዕውር አነ ።
ዕውር ሁኜ እንደተወለድሁ ።
ወይእዜኒ እሬኢ ።
ዛሬ እንደ ዳንሁ ይህን ብቻ አውቃለሁ እንጂ ።

፳፮ ወይቤልዎ ካዕበ ምንተ ገብረ ለከ ።
፳፮ ለቀረበው ካዕበ አለ ፤ ሁለተኛ ምን አደረገልህ ።
ወእፎ ከሠተከ አዕይንቲከ ።
ዓይንህንስ እንደምን አዳነህ አሉት ።

፳፯ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ነገርኩክሙሂ ዳዕሙ ወኢትሰምዑ ወኢተአምኑኒ ።

፳፯ አትሰሙኝም አታምኑኝም እንጂ እኔስ ነገርኋችሁ ።
ምንተ እንከ ትፈቅዱ ካዕበ ትስምዑ ።
ሁለተኛ ምን ልትሰሙ ትወዳላችሁ ።
አንትሙኒ አርዳኢሁኑ ትኩኑ ትፈቅዱ ።
እናንተም የሱ ደቀ መዛሙርት ልትሆኑ ትወዳላችሁን አላቸው ።

፳፰ ወጸአልዎ ፤
፳፰ የዕውር ስድብ ሰደቡት ጠንባሳ ዕውር ብለው ። እንድም ሌላ ስድብ ሰደቡት ።
ወይቤልዎ አንተ ኩን ረድአ ሎቱ ።
አንተ ለርሱ ደቀ መዝሙር ሁነው ።
ወንሕነ አርዳኢሁ ለሙሴ ንሕነ ።
እኛስ የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን ።

፳፱ ወንሕነ ነአምር ከመ ለሙሴ ተናገሮ እግዚአብሔር ገጸ በገጽ ።

፳፱ ሙሴን ቃል ለቃል እንደተነጋገረው እናውቃለን ።
ወለዝንቱሰ ኢነአምሮ እምአይቴ ውእቱ ።
ይኸን ግን ከወዴትም እንደመጣ አናውቀውም አሉ ።

፴ ወአውሥአ ውእቱ ብእሲ ።

፴ ያም ሰው መለሰ ።

ወይቤሎሙ ዓዲ በዝንቱ ጥቀ መንክር ውእቱ ዘኢተአምርዎ አንትሙ እምአይቴ ውእቱ ወከሠተኒ አዕይንትየ ።
ቢሆን ተአምራቱን አይቶ ማመን ይገባ ነበር ።
በዝንቱ ፤

ተአምራቱን አይታችሁ ባለማመናችሁ ላይ ዓይኔን ያዳነኝን ከየትም እንደመጣ የማታውቁትን ኃጥእ ነው ማለታችሁ እጅግ ድንቅ ነው ። አንድም ተመራምሮ ዐውቆ ማመን ይገባ ነበር ፤ ተመራምራችሁ ባለማመናችሁ ላይ እኔን ያዳነኝን ከወዴትም እንደመጣ የማታውቁትን ኃጥእ ነው ማለታችሁ እጅግ ድንቅ ነው ።

፴፩ ወንሕነሰ ነአምር ባሕቱ ከመ ለኃጥአን ኢይሰምዖሙ እግዚአብሔር ።

፴፩ እኛ ኃጥአንን እግዚአብሔር እንዳይቀበላቸው እናውቃለን ።
እመኒ አብዛኅከሙ ምህላከሙ ኢይሰምዓከሙ እግዚአብሔር እስመ ደም ምሉእ ውስተ እደዊክሙ እንዲል ።
ዘእንበለ ዘያፈርሆ ለፈራሂ ወለዘይገብር ፈቃዶ ሎቱ ይሰምዖ ።
የሚፈራውን ፈቃዱን የሚሠራውን ይሰማዋል እንጂ።
ወህሎ አሐዱ ብእሲ ጻድቅ ወፈራሄ እግዚአብሔር ወረከብክዎ ለዳዊት ገብርየ ብእሴ ምእመነ ዘከመ ልብየ እንዲል ።

፴፪ ግሙራ ኢተሰምዓ እምአመ ተፈጥረ ዓለም ከመ ቦ ዘዕውሩ ተወልደ ወተከሥተ አዕይንቲሁ ።

፴፪ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ዕውር ሁኖ የተወለደ ኋላ ዓይኑ ያየ ከቶ ተሰምቶም አያውቅም ይህ ሰው ትውልዱ ከእስራኤል ነው ያሉ እንደሆነ ተወልደን ከአሕዛብ ነው ቢሉ ተከሥተን ይሻል ፤ ከብዛት አንድ አንድ አይታጣምና ።

፴፫ ሶበሰ ኢኮነ እምኀበ እግዚአብሔር ዝንቱ ብእሲ እምኢክህለ ገቢረ ወኢምንተኒ ።

፴፫ ይህ ሰው ደግ ባይሆንስ ተአምራት ማድረግ ባልተቻለውም ነበር ።

፴፬ ወአውሥኡ አይሁድ ወይቤልዎ ዘለሊከ በኃጢአትከ ተወለድከ አንተሁ ትሜህረነ ለነ ።

፴፬ ዘኵነኔ ቀድሞ ባዮች ናቸውና የኋላ ኃጢአትክን ፀውቆ ዕውር አድርጎ ቢፈጥርህ አንተ ለኛ ታስተምራለህ አሉት ።
ወሰደድዎ ወአውፅእዎ አፍአ ከምኵራብ አወጡት ከሰው ለዩት ።

፴፭ ወሰምዓ እግዚእ ኢየሱስ ከመ አውፅእዎ አፍአ ።

፴፭ ከምኵራብ እንዳወጡት ከሰው እንደ ለዩት ጌታ ሰምቶ ።
ወረከቦ ።
አገኘው እኒያ ቢለዩዋችሁ እኔ አልለያችሁም ሲል ።
ወይቤሎ ተአምንሁ አንተ በወልደ እግዚአብሔር ።
አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን አለው ።

፴፮ ወአውሥአ ወእቱ ብእሲ ።
፴፮ ያም ሰው መለሰ ።
ወይቤሎ መኑ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ከመ እእመን ቦቱ ።
እምንበት ዘንድ ወልደ እግዚአብሔር ማነው አለው ።

፴፯ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ዘትሬእዮ ወዘይትናገር ምስሌከ ውእቱ ዝንቱ ።

፴፯ የምታየው ካንተ ጋራ የሚነጋገረው ነው ማለት እኔ ነኝ አለው ።

፴፰ ወይቤ ከሊሆ አመንኩ እግዚኦ ።
፴፰ አምናለሁ ብሎ አሰምቶ ተናገረ ።
ወሰገደ ሎቱ ፤ ሰገደለት ።

፴፱ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አንሰኬ መጻእኩ ለኵነኔ ዝንቱ ዓለም ።

፴፱ እኔ በሰው መፈራረጃ ልሆን መጥቻለሁ ላመነብኝ ልፈርድለት ባላመነብኝ ልፈርድበት ።
ከመ እለ ኢይሬእዩ ይርአዩ የማያዩ ያዩ ዘንድ ማለት ዐላዋቆች ነን የሚሉ ሐዋርያት ዐዋቆች ይሆኑ ዘንድ ልፈርድለት ላለው ።
ወእለኒ ይሬእዩ ይዑሩ ።
ዐዋቆች ነን የሚሉ ጸሐፍት ፈሪሳውያንም ዐላዋቆች ይሆኑ ዘንድ ልፈርድበት ላለው ።

፵ ወቦ እምፈሪሳውያን እለ ሀለዉ ምስሌሁ እለ ሰምዑ ዘንተ ወይቤልዎ ዕውራንኑ ንሕነኬ ።

፵ ከርሱ ጋራ ያለ ከፈሪሳውያን ወገን ይኸን ሰምተው ዕውራን የምትለው እኛን ነውን አሉት ።

፵፩ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ሶበሰ ዕውራን አንትሙ እምኢኮንክሙ ጌጋየ ።

፵፩ ጌታም ዕውራንስ ብትሆኑ ዕዳ ባልሆነባችሁም ነበር እላቸው ነውረ ሥጋ ከመንግሥተ ሰማይ አያወጣምና ።

ወይእዜሰ ንቡር ጌጋይክሙ ።
ጽሑፍ ሲል ነው ዛሬ በደላችሁ ታውቋል ።
እስመ ትብሉ ንሬኢ ወኢትሬእዩ ።
እናውቃለን ትላላችሁ አታውቁምና ።
ወበእንተ ዝንቱ ኢይትኃደግ ለክሙ ጌጋይክሙ ።
ስለዚህ ኃጢአታችሁ አይሰረይላችሁም ።

በእንተ ኖላዊ ኄር ።

ምዕራፍ ፲ ።

፩ አማን አማን እብለክሙ ዘኢቦአ እንተ አንቀጽ ውስተ ዓጸደ አባግዕ ወዓርገ እንተ ካልዕ ገጽ ሠራቂ ወፈያት ውእቱ ።
ስለ ሦስት ነገር ያመጣዋል አንሰ መጻእኩ ለኵነኔ ዝንቱ ዓለም ብሎ ነበርና ለምሕረትም እንደመጣ ለማጠየቅ ፤ ለዝንቱሰ ኢነአምሮ ብለውት ነበር ከየትም እንደመጣ ለማጠየቅ ኄር ኖላዊ አይደለም ብለውታልና ኄር ኖላዊ እንደሆነ ።

፩ ለማጠየቅ ።
እባግዕ ወዳሉበት ቦታ በበር ያልገባ አጥር ጥሶ፡ቅጥር እፍርሶ የገባ ሌባ ወንበዴ ነው ።

፪ ወዘሰ እንተ አንቀጽ ይበውእ ኖላዊ እባግዕ ውእቱ ።

፪ በበር የገባ ግን ባለቤት ነው ።

፫ ወሎቱ ሰዓፃዊኒ ያርኅዎ ፤

፫ ለርሱ በረኛውም ይከፍትለታል ።
ወአባግዕኒ ይሰምዕዎ ቃሎ ።
በጎችም ቃሉን ይሰሙታል ።
ወይጼውዖን ለአባግዒሁ በበአስማቲሆን ።
በጎችንም በየስማቸው ይጠራቸዋል ፤ ሶሬት ቆሬት ቀንዲት እያለ ።
ወያወፅኦን ወያወፍሮን ።
ያወጣቸዋል ያሠማራቸዋል ።

፬ ወሶበ እውፅኦን ወአውፈሮን የሐውር ቅድሚሆን ።

፬ ካወጣቸው ካሠማራቸው በኋላም በፊት በፊት ይሄድላቸዋል ።
ወይተልዋሁ አባግዒሁ ።
በጎችም ይከተሉታል ።
እስመ የአምራ ቃሎ ።
ቃሉን ያውቁታልና ።

፭ ወለነኪርሰ ኢይተልዋሁ ።

፭ ሌላውን ግን አይከተሉትም ።
ጽጋ እላ ይጎይያ እምኔሁ ።
ይሸሹታል እንጂ ።
እስመ ኢየአምራ ቃሎ ፤
ቃሉን አያውቁትምና ፤ የእምራ ቢል የባለቤቱን ባልሆነ ምሳሌ አያስተምርም ብሎ እንደ ሙሴ እባግዕ አማን አማን እያልክ መልስ ፤ ትንቢት ተነግሮለት እግዚአብሔር አብ መስክሮለት ምእመናን ወዳሉበት ወደዚህ ዓለም ያልመጣ ፤ ይህስ እንዳይሆን ወብየ ካልዓትኒ አባግዕ አለ ኢኮና እምዝንቱ ዓጸድ ብሎ ያመጣዋል ። ዓጸድ የተባለች ኢየሩሳሌም ናት ፤ ትንቢት ተነግሮለት እግዚአብሔር እብ መስክሮለት ምእመናን ወዳሉባት ወደ ኢየሩሳሌም በመምህርነት ያልመጣ ወዓርገ ትንቢት ሳይነገርለት እግዚአብሔር እብ ሳይመሰክርለት የመጣ የመምህርነት ሌባ ወንበዴ ነው ። እንደ ይሁዳ ዘገሊላ እንደ ቴዎዳስ ዘግብጽ ። ወዘሰ እንተ አንቀጽ ። ትንቢት ተነግሮለት እግዚአብሔር እብ መስክሮለት የመጣ ግን የመምህርነት ባለቤት ነው ። ወሎቱስ ። እባቱ ይመሰክርለታል ። እንድም መጻሕፍት ዮሐንስ ተአምራት ይመሰክሩለታል ። እንድም እማን ብለሀ መልስ ዓሠርቱ ቃላትን ይዘው በወንጌል ያላመኑ ዓሠርቱ ቃላትን ሳይዙ በወንጌል እናምናለን የሚሉ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ናቸው ። ወዘሰ ። ዓሠርቱ ቃላትን ይዘው እናምናለን የሚሉ ግን ሐዋርያት ናቸው ። ዓጸዊኒ ። እኔ እቀበላቸዋለሁ። እንድም ዘኢቦእ ብለሀ መልስ ። ሕዋሳቱን በስበሰበ ዓሠርቱ ቃላትን በያዘ በሰቂለ ሕሊና በነቂሃ ልቡና በሆነ የማያድር ሕዋሳቱን ባልሰበሰበ ዓሠርቱ ቃላትን ባልያዘ በሰቂለ ሕሊና በነቂሐ ልቡና ሁኖ በሚኖር የማያድር ሰይጣን ነው ። ወዘሰ እንተ እንቀጽ። ሕዋሳቱን ባሰባሰበ ዓሠርቱ ቃላትን በያዘ በሰቂለ ሕሊና በነቂሃ ልቡና በሆነ የሚያድር ግን መንፈስ ቅዱስ ነው ። እጻዊኒ። አእምሮ ይመሰክርለታል እንድም ዘኢቦእ ። በምክረ ካህን የማይኖር በምክረ ርእሱ በፈቃደ ርእሱ የሚኖር ኃጥእ ነው ። ወዘሰ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖር ግን ጻድቅ ነው ። ዓፃዊኒ ። አፃዊ እኔ በዕለተ ምጽእት እቀበለዋለሁ ወዓባግዕኒ ። ሐዋርያት ትምህርቱን ይቀበሉታል ። ወይጼውዖን ። ሐዋርያት ሰብዓ አርድዕት እያለ። እንድም ስምዖንን ጴጥሮስ ልብድዮስን ታዴዎስ ዲዲሞስን ቶማስ እያለ ይጸራቸዋል ። ያወፅኦን ወያወፍሮን ዘኢጾረ መስቀለ ሞትየ ባኡ እንተ ጸባብ እንቀጽ እያለ ያስተምራቸዋል ወሶበ እውፈሮን ካስተማራቸው በኋላም ይሰቀልላቸዋል ። ወይተልዋሁ ። እርሱን አብነት አድርገው መከራ ይቀበላሉ በመከራ ይመስሉታል ። እስመ የእምራ ትምህርቱን ተቀብለውታልና። ወለነኪርሰ የመምህርነት ሌባ ወንበዴውን ግን አብነት እያደርጉትም አይመስሉትም እላ ይጐይያ ። ይነቅፉታል እንጂ። እስመ ኢየእምራ ። ትምህርቱን አይቀበሉትምና ። የእምራ ቢል ለላይኛው ።

፮ ወዘንተ ምሳሌ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ።

፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይኸነን ምሳሌ ነገራቸው ።
ወእሙንቱሰ ኢያእመሩ ዘይቤሎሙ ።
እርሳቸው ግን ኖላዊ የተባለ እርሱ ። እባግዕ የተባሉ እርሳቸው እንደሆኑ ዐላወቁም ።

፯ ወካዕበ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አማን አማን እብለክሙ እነ ውእቱ አንቀጸ አባግዕ ።

፯ ዳግመኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የበጎች ደጅ እኔ ነኝ አላቸው ።

፰ ኵሎሙ እለ መጽኡ እምቅድሜየ ሠረቅት ወፆሕልያ እሙንቱ ።

፰ ከኔ አስቀድሞ የመጡ ሁሉ የመምህርነት ሌባ ወንበዴ ናቸው እንደ ይሁዳ ዘገሊላ እንደ ቴዎ

ዳሰ ዘግብጽ ።
ወባሕቱ ኢይሰምዕዎሙ አባግዕ ።
ነገር ግን አባግዕ ምእመናን አይቀበሏቸውም ።

፱ እነ ውእቱ አንቀጸ አባግዕ ዘበእማን ።
፱ ዘበእማን ለማለት ደገመው እውነተኛ ደጅ እኔ ነኝ ።
ዘቦአ ብእሲ እንተ ኅቤየ ይድኅን ።
በኔ በኩል የገባ ማለት በኔ ያመነ ሰው ከክህደት ይድናል ።
ወይበውእ ፤
ወደ ሃይማኖት ይገባል ።
ወይወፅእ ፤
ሥራ ለመሥራት ይወጣል ።
ወይረክብ ምርአየ ፤
መሰማርያም ያገኛል ማለት እሳቱን ስለቱን መስቀሉን ያገኛል ፤ አንድም እኔን አብነት ያደረገ ፤ ይድኅን ከፍዳ ፤ ወይበውእ ወደወንጌል ፤ ወይወፅእ ። ለማስተማር ፤ ወይረክብ ምርዓየ ። ጕባኤን ፤ አንድም መራዕየ ምእመናንን አንድም እኔን በኵር ያደረገ ይድኅን ፤ ከፍዳ ፤ ወይወፅእ ከፈቃደ ሥጋ ወይበውእ ፤ ወደፈቃደ ነፍስ ።
ወይረክብ ክብረ ሥጋን ክብረ ነፍስን ያገኛል መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል ።

፲ ወሰራቂሰ ኢይመጽእ ዘእንበለ ከመ ይሰርቅ ወይጥባሕ ወያኅጕል ።

፲ ሌባ ግን ሊጐዳ ነው እንጂ ሊጠቅም ሊያጠፋ ነው እንጂ ሊያለማ አይመጣም ፤ አንድም የመምህርነት ሌባ ወንበዴ ግን ሊጐዳ ነው እንጂ ሊጠቅም ሊያጠፋ ነው እንጂ ሊያለማ አይመጣም ።
ወአንሰኬ መጻእኩ ከመ ይርከቡ ሕይወተ ዘለዓለም ።
እኔ ግን የዘለዓለም ድኅነትን ያገኙ ዘንድ ሰው ሆንኩ በመምህርነት መጣሁ ።
ወፈድፋደ ይርከቡ ።
በነፍስ በሥጋ ለማለት ደገመው ይበዛላቸው ዘንድ ።

፲፩ አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር ። ኢሳ፡፵ ፤ ፲፩ ሕዝ፡፴፬ ፡ ፳፫ ።

፲፩ ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ ።
ወኖላዊሰ ኄር ይሜጡ ነፍሶ ቤዛ አባግዒሁ ።
ባለቤት ለበጎቹ ቤዛ ሰውነቱን አሳልፎ ይሰጣል ።

፲፪ ወእሳብስ ዘኢኮነ ኖላዌ ወዘኢኮና አባግዕ ዘዚአሁ ሶበ ይሬኢ ተኵላ እንዘ ይመጽእ ይጐይይ ወየኃድጎን ለአባግዒሁ ።

፲፪ ዓባግዕ ገንዘቦቹ ያይደሉ ጠባቂ ያይደለ ምንደኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ አባግዕን ጥሏቸው ይሸሻል ።
ወእምዝ ይመጽእ ወይመስጥን ተኵላ ።
ከዚህ በኋላ ተኵላ መጥቶ ይነጥቃቸዋል ።
ወይዘርዎን ለአባግዕ ።
በጎችን ይበትናቸዋል ።

፲፫ ወእሳብስ ይጐይይ ።
፲፫ ምንደኛ ግን ይሸሻል ።
እስመ አሳብ ውእቱ ።
ምንደኛ ነውና ።
ወኢያኃዝኖ በእንተ አባግዕ ።
የበጎቹም ጥፋት አያሳዝነውም ፤ አንድም ወኖላዊሰ ኄር ብለህ መልስ ። እውነተኛ መምህር የምሆን እኔ ለምእመናን ቤዛ ራሴን ለሕማም ለሞት አሳልፌ እሰጣለሁ ፤ ወአሳብስ ምእመናን ወገኖቹ ያይደሉ ሐሰተኛ መምህር ግን መናፍቅ ጳጳስ አላዊ ንጉሥ በተነሣ ጊዜ ይከዳል ። ወየኃድግ ፤ ምእመናንን አሳልፎ ይሰጣቸዋል ። እንደ ፎሳቀሲስ ። ወይመሥጠን ይጣላቸዋል ። ወይዘርዎን አገር አስጥሎ ይሰዳቸዋል ፤ ወአሳብስ ፤ ሐሰተኛው መምህር ግን ይከዳል እስመ ሐሳዊ ውእቱ ። ሐሰተኛ ነውና ። ወኢያኀዝኖ ፤ የምእመናን ጥፋት አያሳዝነውምና ።

፲፬ እነ ውእቱ ኖላዊ ኄር ።
፲፬ ቸር ጠባቂ እውነተኛ መምህር እኔ ነኝ ።
ወእአምር ዘዚአየ መርዔትየ ።
በጎቼን አውቃቸዋለሁ ለምእመናን እሞትላቸዋለሁ ።
ወየአምራኒ መራዕይየ ፤
ያውቁኛል ማለት እኔን አብነት አድርገው ምእመናን መከራ ይቀበላሉ ።

፲፭ ወበከመ የአምረኒ አብ ። ማቴ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ሉቃ፡፲ ፡ ፳፪ ።

፲፭ አብ ሙት ተሰቀል እንዳለኝ ።
አነኒ እእምሮ ለአብ ።
እኔም ልሞት ልሰቀል እንደመጣሁ ።
እሜጡ ነፍስየ ቤዛ አባግዕየ ።
ለምእመናን ቤዛ ለሕማም ለሞት አሳልፌ ሰውነቴን እሰጣለሁ ።

፲፮ ወብየ ካልዓትኒ ዓባግዕ እለ ኢኮና እምዝንቱ ዓጸድ ።

፲፮ በዚህ ቦታ የሌሉ ሌሎች በጎች አሉኝ በኢየሩሳሌም የሌሉ ባራቱ ማዕዘን ያሉ ሌሎች አሉኝ
ወኪያሆንኒ ህለወኒ አምጽኦን ዝየ ።
ወደዚህ አመጣቸው ዘንድ ማለት እርሳቸውንም በሃይማኖት አንድ አደርጋቸው ዘንድ አለኝ ፤ ኢጽምዖን ይላል አስተምራቸው ዘንድ ፤
ወይሰምዓኒ ቃልየ ።
ትምህርቴን ይቀበሉኛል ።
ወይከውና አሐደ መርዔተ ለአሐዱ ኖላዊ ።
ላንድ ጠባቂ መንጎች ይሆናሉ ላንድ ለክርስቶስ

አካል ብልት ላንድ ኤጲስቆጶስ ማኅበር ቤተ ስብእ ይሆናሉ ።

፲፯ ወበእንተዝ ያፈቅረኒ አብ እስመ አነ እሜጡ ነፍስየ ቢዛ አባግዕየ ከመ ካዕበ እንሥእ ። ኢሳ፡ ፶፫ ፡ ፯ ።

፲፯ ዳግመኛ እሥነማት ዘንድ ሰውነቴን ለሕማም ለሞት አሳልፌ እሰጣለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል ፤ ያልተካከለ ። ትንሣኤውን ለሞቱ ካዕበ አለ ፤ አንድም የተካከለ ነው ፤ በሕይወት ለመኖሩ ትንሣኤውን ካዕበ አለ ።

፲፰ ወአልቦ ዘየሐይደንያ ፤

፲፰ ያለኔ ፈቃድ ነፍሴን ከሥጋዬ የሚለያት የለም ።

አላ ስልየ እሜጥዋ በፈቃድየ ።
እኔ ወድጄ እለያታለሁ እንጂ ።
እስመ ብውሕ ሊተ እመጥዋ ።
ነፍሴን ከሥጋዬ አለያት ዘንድ ይገባኛልና ።
አንብራሂ ፤
ነፍሴን ከሥጋዬ ለይቼ በገነት ።
ወእሚማ ።
ሥጋዬን ከነፍሴ ለይቼ በመቃብር አኖራት ዘንድ ፤
ወብውሕ ሊተ ካዕበ አንሥአ ።
ደግሞም እሥነሣት ዘንድ ይቻለኛል ። አንድም አንብራ ሥጋዬን በመስቀል እሚማ በመቃብር አንሥአ በትንሣኤ ። አንድም ሥጋዬን ከነፍሴ ለይቼ ሥጋዬን በመቃብር ነፍሴን በገነት አንሥእ በትንሣኤ ። አንድም አንብራሂ ነፍሴን ከሥጋዬ ለይቼ በገነት ሥጋዬን ከነፍሴ ለይቼ በመቃብር ። ወአንሥአ በትንሣኤ ፡ ወእሚማ ፡ በዕርገት በየማነ አብ በፀባነ ኪሩብ ። ወዘንተ ትእዛዘ ነሣእኩ እምኀበ አቡየ ።
አዋሕዶ ማሥነሣትን ካባቴ ገንዘብ አደረግሁ ።

፲፱ ወተናፈቁ እንከ ካዕበ አይሁድ በበይናቲሆሙ በእንተ ዝንቱ ነገር ።

፲፱ ስለዚህ ነገር አይሁድ ዳግመኛ ተለያዩ ኃጥእ ነው ጻድቅ ነው በማለት ተለያይተው ነበርና ፤

፳ ወይቤሉ ብዙኃን እምኔሆሙ ጋኔን እኃዞ ወየኢብድ ምንትኑ ታጸምዕዎ ።
ሎቱ ስብሐት ከርሳቸው ወገን ብዙዎቹ ጋኔን አድሮበት አእምሮውን ይነሣዋል ለምን ትሰሙታላችሁ አሉ ።

፳፩ ወቦ እለ ይቤሉ ዝንቱ ነገር ኢኮነ ዘጋኔን
፳፩ ይህ ነገር ጋኔን ያደረበትም አይደለ ።
ዘጋኔንኑ ይክል አሕይዎ ከሚተ አዕይንቲሆሙ ። ለዕውራን ።

የዕውራንን ዓይን ይከፍት ዘንድ ይችላልን ያሉምአሉ።

ዘከመ ሀሎ ኢየሱስ በበዓለ ሐድሶ ሕንጸት ።

፳፪ ወኮነ በውእቱ መዋዕል ሐድሶ ሕንጸታ ለኢየሩሳሌም ።

፳፪ የኢየሩሳሌም ሕንጻ መታደሻ በዚያ ወራት ነበር ።
ወክረምት ውእቱ ።
ማንሻ ፤ አንድም የኢየሩሳሌም ሕንጻ መታደሻ ወራት ክረምት ነበረ ። አንድም አመ መድቅሐ ይላል ፤ የኢየሩሳሌም ሕንጻ መታደሻ ጊዜ ክረምት ነበር ደቅሐሙ በመድቅሑ እንዲል ፡ ከህነት ከምስፍና አንድ አድርጎ ይዞ የሚኖር አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው ነበር የእኅቶቹ ልጆች ስምዖን አልፍሞስ መባልስ ይባላሉ ሹመት በተራ ሥጋ በገበታ እንዲሉ ፤ ፈንታችንን ሹመን አሉት ። እኔ ከእግዚአብሔር አግኝቼ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው የተሾምኩት ሕዝቡን አስፈቅዳችሁ ተሾሙት አላቸው ሕዝቡን ቢያማክሩዋቸው አባታችን ምንብሎን አኗቸው ጽርእ ወርደው ከአንጥያኮስ ዘንድ ነገሩ የዳዊት የሰሎሞን አገር መንግሥት ጠፍቶብ ቸዋል መጥተህ አትገዛንም አሉት ። ለጊዜው ፈጣሪያችሁ ኃያል ነው እምባችሁ ጽኑ ነው አይሆን ልኝም አላቸው ይህስ አይቸግርህም እንደ አባቴ እንደ እስክንድር በአሪት አምናለሁ መሥዋዕተ በግዕ እሠዋለሁ ለሥዕለ ኪሩብ እሰግዳለሁ እነጥፋለሁ አጋርዳለሁ ብለህ ግባ ከዚህ በኋላ የወደድከውን ታደርጋለህ ብለው መከረው መጥተው እናንተ ሹመት ብትነሡን ከፉ አናደርግም ብለን ጽርእ ወርደን አንጥያኮስን ያህል ሰው አሳምነን እንደ እስክንድር በአሪት እንዲያምን መሥዋዕተ በግዕ እንዲሠዋ ለሥዕለ ኪሩብ እንዲሰግድ አድርገን መጣን አሉ ።
አመሰ አማን ጽድቀ ትነቡ እኋቸው የእስራኤልን በዓል ሁሉ ያውቀዋልና መጥቶ ሰፈረእግቡኝ አለ ። ሕጋችን ኢይባእ ሞዓባዊ ወአሞናዊ ትላለች አይሆንም እሉት ። አያችሁ በእግዚአብሔር አማኒ ሲክለከሉበት አንጥያኮስን ያህል ሰው እንዲህ ቢል እያሉ እየዞሩ ይለፉ ፪መሩ ። ይግባ ባዩ በዛ አንተ ብቻህን ግባ አሉት የጾር ነገር ዓይነተኛው ከገባ አይቀርምና ፊታውራሪ ቀኛዝማች ግራዝማች አያለ አጻፋቸው እስራኤል ዐሥራ ሁለት እልፍ ነበሩ ። እኒያ ፳፪ እልፍ ሆኑ እልዓዛርን አንተ በግ ሠውተህ ብላ ለሕዝቡ እረያ ሠውተህ አብላኝ ። አንተ ለሥዕለ ኪሩብ ስገድ ሕዝቡን ለሥዕለ ፀሐይ አስግድልኝ አለው ፈጣሪዬ ለጥብዓት አብነት ቢያደርገኝ ለፍርሃት ለሃይማኖት አብነት ቢያደርገኝ ለክህደት አብነት አልሆንም

እለው ። ፺ ለከህነት የበቁ ልጆች ነበሩት ከፊቱ በሰይፍ አስመትቷቸዋል ሚስቱን በጡቶችዋ አሰቅሏታል እሱንም ሻሽ በሰም ጠምቶ ከራሱ እስከ እግሩ ሸፍኖ የብረት ምጣድ አግሎ በራሱ ደፋበት ሙቷል በዚህ ጊዜ አራቱ እልፍ ሞቱ አራቱ እልፍ ተማረኩ አራቱን እልፍ ይሁዳ መቃብያዊ ቅጽር አፍርሶ ይዟቸው ወጥቷል ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ኑረው ቢመለሱ የምሥራቁ ከምዕራብ የምዕራቡ ከምሥራቅ ዙሮ የቀኙን ወደግራ የግራውን ወደቀኝ አድርጎ በግዕ በሠውበት አሪያሠውቶበት ሥዕለ ኪሩብ ባቆሙበት ሥዕለ ፀሐይ አቁሞበት አገኙት ኀልዳና የምትባል ነቢይት ነበረች ሂደው እንዲህ ሁኖ አገኘነው እንደምን እናድርግ አሏት ጠርጋችሁ ጥላችሁ ያን ደልድላችሁ አሪያ በሠውበት በግ ሠውበት ሥዕለ ፀሐይ ባቆሙበት ሥዕለ ኪሩብ አቁሙበት ብላቶቸለች ይህ ሲያያዝ ከጌታችን ክኢየሱስ ክርስቶስ ደርሷል ።

፳፫ ወእንሶሰወ እግዚእ ኢየሱስ በቤተ መቅደስ በሕዋረ ሰሎሞን ።

፳፫ ሰሎሞን በሠራው በብረት መመደብ በቤተ መቅደስ ተመላለሰ አንድም ። በእምስቱ በስድስቱ በሰባቱ ቆመ ብእሲ ተመላለሰ ።

፳፬ ወዓገትዎ አይሁድ ወይቤልዎ እስከ ማእዜኑ ታመነድበነ ነፍሰነ ።

፳፬ አይሁድ ከበው ይዘው እስከመቸ ሰውነታችንን ታስጨንቃለህ ትነሥእነ ይላል እስከ መቸ ድረስ ስታስቅቀን ትኖራለህ ።
ለእመ አንተሁ ክርስቶስ ንግረነ ገሃደ ።
ክርስቶስ አንተ እንደሆንክ ገልጠህ ንገረን ።

፳፭ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፳፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ነገርኩክሙ ።
እኔስ ነገርኳችሁ ።
ወኢተአምኑኒ ወኢትሰምዑኒ አትቀበሉኝም እንጂ ።
ግብር ዘእገብር አነ በስመ አቡየ ውእቱ ሰማዕትየ ።
ግብር ማንሻ ። አንድም እኔ ብነግራችሁ ባትቀበሉኝ ። ባባቴ ስም የምሠራው ሥራ ምስክሬ ነው ።

፳፮ ወአንትሙሰ ኢተአምኑኒ ።
፳፮ እናንተ ግን አትቀበሉኝም
እስመ ኢኮንክሙ እምነ አባግዕየ ።
ከምእመናን ወገን አይደላችሁምና ፤ በከመ እቤለክሙ ፤ ከምእመናን ወገን አይደላችሁም ብዬ እንደ ነገርኳችሁ ። አንድም ወአንትሙሰ ፤ ከምእመናን ወገን አይደላችሁምና ትምህርቴን አትቀበሉኝም ።

፳፯ አባግዕየሰ እሊአየ ይሰምዓኒ ቃልየ ።
፳፯ ወገኖቼ ምእመናን ትምህርቴን ይቀበሉኛል ብዬ እንደ ነገርኳችሁ ፥ ይሰምዓኒ ብለህ እስር ።
ወእነሂ ። እአምሮን ።
እኔም ዐውቃቸዋለሁ ማለት እሞትላቸዋለሁ ።
ወይተልዉኒ እማንቱ ድኅሬየ ።
እርሳቸውም እኔን አብነት አድርገው መከራ ይቀበላሉ ።

፳፰ ወእነሂ እሁቦን ሕይወተ ዘለዓለም ።
፳፰ እኔም የዘለዓለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ የማታልፍ መንግሥተ ሰማያትን አወርሳቸዋለሁ ።
ወኢይትኃጐላ ለዓለም ።
ለዘለዓለም ጉዳት አያገኛቸውም
ወአልቦ ዘየሐይደንዮን እምእዴየ ።
ከኔ አንድነት የሚለያቸው የለም ።

፳፱ እስመ አቡየ ዘወሀበኒዮ ውእቱ የዓቢ እምኵሉ ።

፳፱ እርሳቸውን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል ማለት የባሕርይ አምላክ ነው ።
ወአልቦ ዘይክል ሐይደ ወመሢጠ እምእዴሁ ለአቡየ
ካባቴ እጅ ይነጥቃቸው ዘንድ ማለት እዱ መዝራዕቱ ከተባልሁ ከኔ አንድነት የሚለያቸው የሰም ።

፴ አነ ወአብ ፩ዱ ንሕነ ።
፴ እኔና አባቴ ፩ ነን በሥልጣን በብርሃን በቅዳሴ ፥ እስመ ስብሐተ አብ ስብሐተ ወልድ ወስብሐተ መንፈስ ቅዱስ እንዲል ።

በእንተ ጽልዕ ዘአይሁድ ላዕለ ኢየሱስ ።

፴፩ ወነሥኡ እብነ ካዕበ አይሁድ ከመ ይውግርዎ ።

፴፩ ዳግመኛ ሊጣሉት ደንጊያ አነሡ ። ፈረንጅ እነ ወእብ አሐዱ ንሕነ ያለው ኃዳሪ ።
እብ የእብየኒ ያለው ማኅደር ነው ይላል ወነሥኡ እብነ ከመ ይውግርዎ ባለው ይረታል ።

፴፪ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፴፪ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ብዙኃ ግብረ ሠናየ አርአይኩክሙ ዘእምኀበ አቡየ ።
ካባቴ በሀልውና ያገኘሁትን ብዙ ትምህርት አስተማርኋችሁ ብዙ ትሩፋት ሠራሁላችሁ ብዙ ተአምራት አደረግሁላችሁ ።
በአይ ግብር እምኔሆሙ ትዌግሩኒ ።
ከሦስቱ በማናቸው ልትጣሉኝ ትወዳላችሁ አላቸው ።

፴፫ ወአውሥኡ አይሁድ ።
፴፫ አይሁድም መለሱ ።

ወይቤልዎ በእንተ ሠናይሰ ግብርከ ኢንዌግረከ ።
በትሩፋትህስ በተአምራትህስ አንጣላህም ።
ወባሕቱ በእንተ ጽርፈትከ ።
በትምህርትህ ነው እንጂ ።
እስመ እንዘ ሰብእ አንተ እግዚአብሔርሃ ትሬሲርእሰከ ።
ሰው ስትሆን አምላክ ነኝ ብለህ ታስተምራለህና ።

፴፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፴፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መለሰ ።
መዝ ፹፩ ፥ ፮ ።
ወይቤሎሙ አኮኑ ጽሑፍ ውስተ ኦሪትክሙ አንስ እቤ አማልክት እንትሙ ።
እኔ አማልክት ናችሁ አልኩ የሚል በኦሪታችሁ ተጽፎ የለምን አላቸው ፤ ይህንማ ዳዊት አይደለም የተናገረው ስለምን ኦሪት አለው ቢሉ ፤ መጻሕፍተ ሐዲሳትን በመከብባቸው ወንጌል እንዲላቸው መጻሕፍተ ብሉያትንም በመከብባቸው ኦሪት ይላቸዋልና ፤ ሰማዕነ በውስተ ኦሪት ከመ ለዓለም ይነብር ክርስቶስ እንዳለ ዳንኤልን ኦሪት ብሎ ወበውስተ ኦሪትኒ ይብል በካልዕ ልሳን ወበካልዕ ከናፍር እትናገሮሙ ለዝ ሕዝብ እንዳለ ኢሳይያስን ኦሪት ብሎ ፤

፴፭ ወሶበ ለእልክቱ አማልክት ይቤሎሙ እለ እስተርአየ ወኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀቤሆሙ ።

፴፭ ቃለ እግዚአብሔር ያደረባቸውን ቃለ እግዚአብሔር የተገለጸላቸውን እኒያን አማልክት ናቸው ካሏቸው አማልክት እንደሆኑ ከተናገሩላቸው ።
ወኢይትከሃል ይትነሠት ወይትሐሰው ቃለ መጻሕፍት ።
መጽሐፍ የተናገረው አይፈርስ አይታበል ።

፴፮ ዘቀደሶ አብ ወፈነዎ ውስተ ዓለም እፎ እንከ ትብሉኒ ትጸርፍ ለእመ እቤለክሙ ወልደ እግዚአብሔር አነ ።

፴፮ ልኮ ያዋሐደኝ እኔ አምላክ ነኝ ብላችሁ ትሳደባለህ ለምን ትሉኛላችሁ ።

፴፯ ወእመሰ ኢይገብር ግብሮ ለአቡየ ኢትእመኑ ብየ ።

፴፯ ያባቴን ሥራ ካልሠራሁ ልትቀበሉኝ አይገባም ።

፴፰ ወእመሰ እገብር ግብሮ ለእመ ኢያየ ኢአመንክሙ ለግብርየ እመኑ ።
፴፰ ያባቴን ሥራ ግን ከሠራሁ ሰውነቴን አይታችሁ ባታምኑ ሥራዬን አይታችሁ እመኑ ፤ ይህን ሥራ አምላክ ሰው ሁኖ ቢሠራው ነው እንጂ ዕሩቅ ብእሲ ይህን አይሠራውም ብላችሁ ።

ከመ ታእምሩ ወትጠይቁ ከመ አነ በአብ ወአብ ብየ እኔ በአባቴ አባቴ በኔ ህልው እንደሆነ ታውቁ ትረዱ ዘንድ ።

፴፱ ወፈቀዱ አይሁድ ካዕበ ከመ የአኃዝዎ ።
፴፱ ዳግመኛ አይሁድ ሊይዙት ወደዱ ።
ወአምሠጠ እምእደዊሆሙ ።
አልተያዘም ፤ ወአምሠጠ ዳዊት ውስተ እደ ኢሎፍሊ እንዲል ።

፵ ወሖረ ካዕበ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ብሔረ ኀበ አጥመቀ ዮሐንስ ቀዲሙ ።

፵ ዮሐንስ ቀድሞ ያጠምቅበት ወደነበረ ወደ ዮርዳኖስ ዳር ዳግመኛ ሄደ ።
ወነበረ ህየ ።
ከዚያም ተቀመጠ ።

፵፩ ወብዙኃን እለ ሖሩ ኀቤሁ ።
፵፩ ብዙ ሰዎችም ወደርሱ ሄዱ ።
ወይቤሉ ዮሐንስ አልቦ ዘገብረ ለነ ተአምር ወኢምንተኒ ።
ዮሐንስ ምንም ምን የሠራልን ተአምራት የለም ።

፵፪ ወባሕቱ ኵሉ ዘይቤ ዮሐንስ በእንተዝ ብእሲ እሙነ ኮነ ።

፵፪ ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገረው ነገር እውነት ሆነ እንጂ ቦታውን ቢያዩ ትዝ ብሏቸው ።
አንድም ከራሳቸው እንቅተው ።
ወብዙኃን እለ አምኑ ቦቱ በህየ ።
በዚያም ያመኑበት ብዙ ናቸው ።

ዘከመ አንሥአ ኢየሱስ ለአልዓዛር ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘይደዊ ዘስሙ አልዓዛር በቤታንያ ዘሀገረ ማርያ ወማርታ ።
አን ወአብ አሐዱ ብሎ ነበርና ነገሩን በሥራው ለማስረዳት ያመጣዋል ። እስመ ሰምዓ ቃላቲሁ ምግባሩ ውእቱ እንዲል ።

፩ የማርያ የማርታ አገር በምትሆን በቤታንያ የታመመ አልዓዛር የሚባል ሰው ታሞ ነበር ። ከሞተ ብሎ ለሙት የለው መብት እንዲሉ ። አንድም አባታቸው ለሙቅ ለመቀነት ይሁናችሁ ብሎ ለይቶ ሰጥቷቸው ነበርና አንድም ባባት አይገናኙምና ዘሀገረ ማርያ ወማርታ አለ ።

፪ ወማርያሰ ይእቲ እንተ ቀብዓቶ ዕፍረተ ለእግዚእነ ። ማቴ፡፳፮፡፮ ሉቃ፡፯ ፴፯ ዮሐ፡፲፪፡ ፫፡
፪ ማርያ ግን ጌታን ሽቱ የቀባችው ናት ።
ወመዝመዘት እገሪሁ በሥእርታ ።
እግሩን በጸጉሯ ያበሰችው ናት ።

ወእኁሁ ላቲ አልዓዛር ይደዊ ።
ወንድሟ አልዓዛር ታሞ ነበር ።

፫ ወለእካ አኃቲሁ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይብላ እግዚእነ ናሁ ዘታፈቅር ይደዊ ።

፫ ጌታ ሆይ ወዳጅህ ታሟል ብለው ወደ ጌታ ላኩ

፬ ወሰሚዖ እግዚእ ኢየሱስ ይቤ ዝንቱ ደዌ ኢኮነ ለሞት ።

፬ ጌታም እንደታመመ ሰምቶ በሰማ ጊዜ ይህ ደዌ ለሞት የሚያበቃ አይደለም ፣ እንድም ሙቶ ሊቀር አይደለም ።

አላ በእንተ ሰብሐተ እግዚአብሔር ።
በልጁ ህልው ሁኖ እርሱን አሥነሥቶ የእግዚአብሔር አብ ጌትነቱ ይገለጥ ዘንድ ነው እንጂ ።
ወከመ ይሰባሕ ወልደ እግዚአብሔር በእንቲአሁ ።
የእግዚአብሔር ልጅ እርሱን አሥነሥቶ በጌትነት ይገለጥ ዘንድ ነው እንጂ ።

፭ ወያፈቅሮን እግዚእ ኢየሱስ ለማርያ ወለማርታ እኅታ ወለአልዓዛር ።

፭ ማርያና ማርታን አልዓዛርንም ጌታ የፍጹማን ፍቅር ይወዳቸው ነበር ።

፮ ወሶበ ሰምዓ ከመ ይደዊ ነበረ ህየ ኀበ ሀለወ ብሔረ ሰኑየ መዋዕለ ።

፮ እንደ ታመመ ሰምቶ ካለበት ቦታ ሁለት ቀን ተቀመጠ ።
ሐተታ ረቡዕ ይሞታል ገሥግሠው ገብተው ይነግሩታል ረቡዕ እንድ ሐሙስ ሁለት ዓርብ ቀርቦ እድሮ ቅዳሜ ገብቶ ያሥነሣዋል ። እንድም ረቡዕ ተሸኝተው አድረው ሐሙስ ገቡ ሐሙስ እንድ ዓርብ ሁለት ቅዳሜ ካለበት ገሥግሦ ገብቶ ያሥነሣዋል ።

፯ ወእምዝ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ንዑ ንሑር ብሔረ ይሁዳ ካዕበ ።

፯ ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ይሁዳ እንሂድ አላቸው

፰ ወይቤልዎ አርዳኢሁ ረቢ ይእዜ የኃሥሡ አይሁድ ይውግሩከ ።

፰ ደቀ መዛሙርቱም አሉት አይሁድ ሊወግሩህ ይሹህ ነበሩ ።
ወካዕበ ትፈቅድ ሐዊረ ህየ ።
ዳግመኛ ልትሄድ እንደምን ትወዳለህ እንደምን ልሂድ ትላለህ አሉት አዝነውለት ። እንድም ዩራሳቸው ፈርተው ።

፱ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ እኮኑ ፲ ወ፪ ሰዓቱ ለዕለት ።

፱ ጌታም ሰዓት መዓልቱ ፲፪ አይደለምን ፲፪ ነውና ።

ብእሲ ዘየሐውር መዓልተ ኢይትዓቀፍ ።
ማንም በቀን የሚሄድ መሰናክል የለበትም ።
እስመ ይሬኢ ብርሃና ለዝንቱ ዓለም ።
የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና ።

፲ ወዘሰ የሐውር ሌሊተ ይትዓቀፍ ።

፲ በሌሊት የሚሄድ ግን መሰናክል አለበት።
እስመ አልቦ ውስቴቱ ብርሃን ዘይሬኢ ።
የሚያየው ብርሃን የለምና ። ጨረቃ ያለች አይደለምን ቢሉ እንደ ፀሐይ አትሆንምና እንድም የጠፋን መናገር ነው ። እንድም ብእሲ ዘየሐውር መዓልተ እያልክ መልስ ። በኔ ባመነ እኔን አብነት ባደረገ ዕቅፍተ ነፍስ የለበትም ። እስመ ይሬኢ ብርሃና ፣ በኔ አምኑዋል እኔን አብነት አድርጓልና ። ወዘሰ የሐውር ሌሊተ በኔ ባላመነ እኔን አብነት ላደረገ ግን ዕቅፍተ ነፍስ አለበት ። እስመ አልቦ ውስቴቱ ብርሃን ፣ በኔ አላመነም እኔን አብነት አላደረገምና ። እንድም ለአርሱ አዝነውለት ላለው ፲፪ ሰዓተ መዓልት ሳይፈጸም ሰዓተ ሌሊት እንዳይመጣ የምሞትበት ጊዜ ሳይደርስ አይጣሉኝም። እስመ ይሬኢ ። የምሞትበት ጊዜ ገና ነውና ። ወዘሰ የሐውር ። የምሞትበት ጊዜ የደረሰ እንደሆነ ይጣሉኛል ። እስመ እልቦ ። የምሞትበት ጊዜ ደርሷልና ልጅነት ያገኘንበትን ከፍዳ የነጸንበትን ሞቱን ስለምን በዕቅፍት መሰለውቢሉ ዕንቅፋት የመታው ሰው ለጊዜው ተግ ይላል ኋላ ግን ይሄዳል ። እርሱም ፫ ሌሊት ፫ መዓልት በከርሠ መቃብር ኑሮ ፈጥኖ ተነሥቷልና ። ወእሕጸረ ዕድሜ ለርእሱ እንዲል ። እንድም ለራሳቸው ፈርተው ላለው ፲፪ ሰዓተ መዓልት ሳይፈጸም ሰዓተ ሌሊት እንዳይመጣ እኔ ሳለሁ አይጣሏችሁም ። እስመ ይሬኢ ፤ እኔ አለሁና ፤ ወዘሰ የሐውር ፤ እኔ የሞትኩ እንደ ሆነ ግን ይጣሏችኋል ። እስመ አልቦ ፤ እኔን አያዩምና ፤ እንድም በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖር ዕቅፍተ ነፍስ የለበትም በምክረ ካህን ይኖራልና ። ወዘሰ የሐውር ሌሊተ በምክረ ርእሱ በፈቃደ ርእሱ በሚኖር ግን ዕቅፍተ ነፍስ አለበት እስመ አልቦ ። በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን አይኖርምና ።
ወዘንተ ነገረ ይቢሎሙ ለአርዳኢሁ ።
ለደቀ መዛሙርቱ ይህን ነገራቸው ።

፲፩ ወእምዝ ይቤሎሙ አልዓዛር ዓርክነ ኖመ ።

፲፩ ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቷል ወባሕቱ እሐውር እንቅሖ ።
ነገር ግን ላሥነሣው እሄዳለሁ አላቸው ።

፲፪ ወይቤልዎ አርዳኢሁ እግዚእ እመሰ ኖመ ይነቅሕ ወይጥዒ ።

፲፪ ደቀ መዛሙርቱም ከተኛስ ዕንቅልፉን ፈጅቶ ጤና ገዝቶ ይነሣል አሉት የታመመ ሰው የተኛ እንደሆነ ጤና ገዝቶ ይነሣል ይባላልና ።

፲፫ ወእግዚእ ኢየሱስ ይቤ በእንተ ንዋመ ሞቱ ።

፲፫ ጌታ ግን ሞት ስለሚባል ዕረፍቱ ነገራቸው ።
ወሎሙስ መሰሎሙ በእንተ ንዋመ ድቃስ ዘይቤሎሙ ።
ለርሳቸው ግን ዕንቅልፍ ስለሚባል ዕረፍቱ የነገራቸው መሰሏቸው ነበር ።

፲፬ ወእምዝ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ገሃደ አልዓዛር ዓርከነ ሞተ ።

፲፬ ከዚህ በኋላ ገልጦ አልዓዛር ወዳጃችን ሞተ አላቸው ።

፲፭ ወአንሰ እትፌሣሕ በእንቲአከሙ ።
፲፭ እኔ ግን ስለእናንተ ደስ ይለኛል ።
እስመ ኢሀሎኩ ህየ ።
እኔ ከዚያ የለሁምና ።
ከመ ትእመኑ አንትሙ ።
እናንተ ታምኑ ዘንድ አስቀድሞ ዐውቆ የነገረን የባሕርይ አምላክ ቢሆን እንጂ ነው ብላችሁ ።
ወባሕቱ ንዑ ንሑር ኀቤሁ ።
ነገር ግን ኑ ወደርሱ እንሂድ ።

፲፮ ወይቤሎሙ ቶማስ ዘይብልዎ ዲዲሞስ ለቢጹ ለአርዳእ ንሑርኬ ንሕነኒ ከመ ንሙት ምስሌሁ ።

፲፮ ንሑር ምስሌሁ ከመ ንሙት ምስሌሁ ። ዲዲሞስ የተባለ ቶማስ ወንድሞቹን ሐዋርያትን እኛም ከርሱ ጋራ እንደርሱ እንሞት ዘንድ እንሂድ አላቸው ፤ ሹመት ሽልማት እናገኛለን ብለን ተከትለነው ነበር ሹመቱን ሽልማቱን ሳናገኝ እንሙት ፤ የቆላ በሬ ጤፉን ሳይበሉ ጣፊያውን እንዲሉ ።

፲፯ ወሖረ እግዚእ ኢየሱስ ቢታንያ ።
፲፯ ጌታ ወደ ቢታንያ ሄደ ።
ወበጺሖ ህየ ረከበ በዘወድአ ረቡዓ መዋዕለ እምዘ ተቀብረ ።
ከዚያም በደረሰ ጊዜ ከተቀበረ አራት ቀን ሆኖት አገኘ ።

፲፰ ወቢታንያሰ ቅርብት ይእቲ ለኢየሩሳሌም መጠነ ፲ወ፭ቱ ምዕራፍ ።
፲፰ ቢታንያ ግን ከኢየሩሳሌም ዓሥራ አምስት ምዕራፍ ትቀርብ ነበረች ።

፲፱ ወብዙኃን እምነ አይሁድ አለ ሖሩ ኀበ ማርያ ወማርታ ከመ ያሳቅስዎን በእንተ እኁሆን ።

፲፱ ወንድማቸው አልዓዛር ስለሞተ ሲያለቅሱለት ወደማርያና ወደማርታ የመጡ አይሁድ ብዙ ናቸው ።

፳ ወሰበ ሰምዓት ማርታ ከመ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ወፅአት ወተቀበለቶ ።

፳ ማርታም ጌታ እንደመጣ በሰማች ጊዜ ወጥታ ተቀበለችው ።
ወማርያሰ ነበረት ቤተ ።
ተርፈት ሲል ነው ወነበረት ውስተ ኢየሩሳሌም እንዲል ማርያ ግን ከቤት ቀረች ፤ ስው ከቤት አስ ቀምጦ መውጣት አይገባምና ።

፳፩ ወትቤሎ ማርታ ለእግዚእ ኢየሱስ ሶበሰ ሀሎከ ዝየ እምኢሞተ እኁየ ።

፳፩ ማርታም ጌታዬ ከዚህ ኑረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር ።

፳፪ ወይእዜኒ አእምር ከመ ዘሰአልኮ ለእግዚአብሔር ይሁበከ እግዚአብሔር ።

፳፪ እግዚአብሔር የለመንከውን እንዲያደርግልህ አውቃለሁና ። ድውይ መፈወስ እንጂ ሙት ማንሣት የማይቻለው መሰሏት ።

፳፫ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ እኁኪሰ ይትነሣእ ።

፳፫ አንች አላመንሽም እንጂ ወንድምሽስ ይነሣል አላት ።

፳፬ ወትቤሎ ማርታ አአምር ከመ ይትነሣእ አመ ትንሣኤ ሙታን በደኃሪት ዕለት ። ሉቃ፥፲፬ ፥ ፲፭ ዮሐ፥ ፭ ፥ ፳፱ ።

፳፬ የኋላውን የነገራት መሰሏት በዕለተ ምጽአት ሙታን በሚነሡበት ጊዜ እንዲነሣ ዐውቃለሁ ። ትውልዷ ከፈሪሳዊ ነው ቢሉ የተመቸ ፤ ከሰዱቃውያን ነው ቢሉ ሲሉ ሰምታ ።

፳፭ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ አነ ውእቱ ትንሣኤ ወሕይወት ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐዩ ። ዮሐ፥፮ ፥ ፵ ።

፳፭ ትንሣኤ ሕይወት እኔ ነኝ ያመነብኝ ቢሞትም ይድናል ማለት ትንሣኤ ዘጉባኤን የማልጠብቅ ባልኩ ጊዜ የማሥነሣ እንድም ሶበስ ሀሎከ ዝየ ብለህ መልስ ፤ አምናለችና ብሎ አንተ ከዚህስ ኑረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር ። ወይእዜኒ አአምር ። አሁንም የለመንከውን እንዲያደርግልህ ዐውቃለሁ ፤ ወይቤላ እኁኪሰ ፤ አንችም አምነሻል ወንድምሽም

ይነሣል አላት ። ወትቤሎ አአምር ፤ ሙታን እንደ ሚነሡት ያለ ትንሣኤ እንዲነሣ ዓውቃለሁ ፤ ወይቤላ አነ ውእቱ አይለውጥም ፤ ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐዩ ፤ በኔ ያመነ አይሞትም በሥጋ ቢሞት በነፍስ ይድናል ፈርሶ በስብሶ አይቀርም ትንሣኤ ዘለክብር ይነሣል ።

፳፮ ወኵሉ ዘሕያው ወየአምን ብየ ኢይመውት ለዓለም ።

፳፮ በሕይወተ ሥጋ ሳለ በኔ ባመነ ሞተ ነፍስ ሙቶ መቅረት የለበትም ።
ተአምኒኑ ዘንተ ።
ሙት ማሥነሣት እንዲቻለኝ ታምኛለሽን አላት ።

፳፯ ወትቤሎ እወ እግዚኦ አንሰ እአምን ከመ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ዘመጽአ ውስተ ዓለም ።

፳፯ አወን አቤቱ እኔስ እስከ ክርስቶስ ተብሎ የተነገረልህ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ አንተ እንደሆንክ አምናለሁ አለችው ።

፳፰ ወዘንተ ብሂላ ጸውዓታ ለማርያ እኅታ ጽሚተ ።

፳፰ ይህን ተናግራ ማርያን እኅቷን ሰውራ ጠራቻት በደግ ሰው ልማድ ።
ወትቤላ ናሁ መጽአ ሊቅነ ወይጼውዓኪ ።
እነሆ መምህራችን መጥቶ ይጠራሻል አለቻት ።

፳፱ ወሶበ ሰምዓት ማርያ ተንሥአት ፍጡነ ወሖረት ኀቤሁ ።

፳፱ እርሷም ማርያ ይህነን በሰማች ጊዜ ፈጥና ተነሣች ወደርሱም ሄደች እኅቷን ተከታ ።

፴ ወዓዲሁ ኢቦአ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ሀገር ።

፴ ጌታም ገና ከከተማው አልገባም ነበር ።
አላ ሀሎ ውስተ መካን ኀበ ተቀበለቶ ማርታ ።
ማርታ ካገኘችው ቦታ ነበር እንጂ ፤ በብዙ ጻዕር እንጂ አሥነሣው እንዳይሉት ።

፴፩ ወሶበ ርእይዋ ለማርያ አይሁድ እለ ሀለዉ ምስሌሃ ውስተ ቤት እለ ያላቅስዋ ከመ ተንሥአት ፍጡነ ወወፅአት ተለውዋ ።

፴፩ ሊያለቅሱለት የመጡ ከርሷ ጋራ ያሉ አይሁድ ፈጥና ተነሥታ እንደሄደች ባዩ ጊዜ ተከተሏት ።
ወመሰሎሙ ዘተሐውር ኀበ መቃብሩ ትብክዮ በህየ ።
ልታለቅስለት ወደ መቃብር የምትሄድ መሰሏቸው ነበር በሦስተኛው ቀን መቃብር ከፍተው መግነዝ ፈትተው ሽቱ እየቀቡ ያለቅሳሉና ።

፴፪ ወሶበ በጽሐት ማርያ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወርእየቶ ወሰገደት ሎቱ ታሕተ እገሪሁ ።

፴፪ ማርያም ጌታም ካለበት ደርሳ ባየችው ጊዜ ከእግሩ በታች ሰገደች ።
ወትቤሎ እግዚእየ ሶበሰ ሀሎከ ዝየ እምኢሞተ እኁየ ።
ጌታዬ ከዚህስ ኑረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር አለችው አሷም እንደ እኅቷ ።

፴፫ ወሶበ ርእያ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ትበኪ ።
፴፫ ጌታም ስታለቅስ ባያት ጊዜ ።
ወአይሁድኒ እለ መጽኡ ምስሌሃ ከመ ይበክዩ ።
ከርሷም ጋራ ያሉ ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ ገዓረ በመንፈሱ ።
በልቡናው አዘነ ።
ወሆሰ ርእሶ ።
ራሱንም ነቀነቀ ፤ መፍቀሬ ሰብእ ነውና ፤ አንድም ሕጸጻቸውን ዓውቆ ፤

፴፬ ወይቤ አይቴ ቀበርክምዎ ።
፴፬ የት ቀበራችሁት አላቸው ፤ ሐዲስ መቃብር አይደለምን ይታወቅ የለም ቢሉ የሀገራቸው መቃብር ሕንጻ ነው ዕለት አይቆፈርም አይታወቅምና ፤ ያስ ቢሆን ይታወቅ የለም ቢሉ ዐላዋቂ ሥጋን እንደተዋሐደ ለማጠየቅ ።
አኮ ኢያእሚሮ ኀቡአተ አላ ከመ የሀብ መካነ ለጥንተ ትስብእቱ ዘኢየአምር ኅቡአተ እንዲል ። አንድም ሳይጠይቅ አሥነሥቶት ቢሆን ምትሐት ነው ባሉት ነበርና ፤ አንድም አይቴ ቀበርክምዎ ለእልዓዛር የሚል ሥጋን ተዋሕጄ አድንኃለሁ ሲል አይቴ ሀሎከ አዳም ብሎት ነበርና ያ እንደ ተፈጸመለት ለማጠየቅ ፤ አንድም ለምንት ሲል ነው ።
ከሱማናይት ትብሱ ይች ስንኳ ልጅዋ ቢሞትባት ዐፅባ አጕናጽፋ አልጋ አስተኝታ ኤልሣዕን ልትጠራ ሄደች ።
ወይቤልዎ እግዚኦ ነዓ ትርኣይ ።
አቤቱ መጥተህ እይ አሉት ።

፴፭ ወአንብአ ካዕበ እግዚእ ኢየሱስ ።
፴፭ ጌታም ዕንባውን አፈሰሰ ።

፴፮ ወይቤሉ አይሁድ ርእዩ መጠነ ያፈቅሮ ።
፴፮ አይሁድም እንዲወደው መጠን ታያላችሁን አሉ ።

፴፯ ወቦ እምውስቴቶሙ እለ ይቤሉ እምኢ ክህለኑ ዝንቱ ዘከሠተ አዕይንቲሁ ለዘዕውሩ ተወልደ ከመ ይግበር በዘኢይመውት ዝንቱኒ ። ዮሐ፡ ፱ ፡ ፮ ።

፴፯ ዕውር ሆኖ የተወለደውን የዚያን ዓይን ያበራ ይህ ከዚህ ኖሮ ቢሆን ይህንስ እንዳይሞት ማድረግ ባልተቻለውም ነበር ዳሩ ምን ይሆናል

ሞተና አሉ ድውይ መፈወስ እንጂ ሙት ማንሣት የማይቻለው መስሏቸው ።

፴፰ ወካዕበ ተከዘ በመንፈሱ እግዚእ ኢየሱስ ።

፴፰ ጌታም ሁለተኛ በልቡ አዘነ ።
ወሖረ ኀበ መቃብሩ እንዘ ያንብዕ ፤
ወደ መቃብሩም እያለቀሰ ሄደ ።
ወበዓት ውእቱ ።
መቃብሩ ሕንጻ ነበር ፤
ወከዱን በእብን ዓቢይ ።
ታላቅ ደንጊያም ተገጥሞ ነበር ።

፴፱ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አዕትትዋ ለእብን እምአፈ መቃብር ።

፴፱ ደንጊያውን አንሡት አላቸው ።
ወትቤሎ ማርታ እኅቱ ለዘሞተ እግዚእየ ናሁ ወፅአ ጼዓ ።
የሞተው እኅት ማርታ ጌታዬ እነሆ ፈጽሞ ተልቷል አለችው ።
እስመ ረቡዓ ኮነ ዮም ።
ዛሬ አራት ቀን ሆኖታልና ።

፵ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ኢይቤለኪኑ ከመ እመ ተአመንኪ ትሬእዪ ስብሐተ እግዚአ ብሔር ።

፵ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ብታምኝ ወንድምሽ እንዲነሣ ነግሬሽ አልነበረምን አላት ።
ወአዕተትዋ ለይእቲ እብን እምአፈ መቃብር ።
ደንጊያይቱን አነሡ ።

፵፩ ወአንሥአ እግዚእ ኢየሱስ አዕይንቲሁ ላዕለ ።

፵፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይኑን ወደ ሰማይ አቀና ፤ ይህን የማሥነሣበት ሥልጣን ካንተ ጋር አንድ ነው ሲል ፤ አንድም ተአምራት ይደረግልን ባላችሁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር አመልክቱ ለማለት አብነት ለመሆን ።
ወይቤ አአኵተከ አባ ።
አባቴ አመሰግንሃለሁ ።
እስመ ሰማዕከኒ ።
ከዚህ አስቀድሞ ልመናዬን ሰምተኸኛልና ።

፵፪ ወአአምር ከመ ዘልፈ ትሰምዓኒ ።

፵፪ አሁንም እንድትሰማኝ ዐውቃለሁና ።
ወባሕቱ በእንተ አለ ይቀውሙ ሰብእ እብል ዘንተ ከመ ይእመኑ ከመ አንተ ፈነውከኒ ።
ነገር ግን ከዚህ ቆመው ስላሉ ሰዎች ይህን እናገራለሁ ፤ ባንተ ፈቃድ ሰው እንደሆንኩ ያውቁ ዘንድ ።

፵፫ ወዘንተ ብሂሎ ከልሐ በዓቢይ ቃል ።

፵፫ ይህን ተናግሮ አሰምቶ ተናገረ ።
ወይቤ አልዓዛር አልዓዛር ነዓ ፃእ አፍአ ።
አልዓዛር አልዓዛር ና ውጣ አለው ፡ ለዕብራውያን ደጊመ ቃል ልማድ ነውና ። አብርሃም አብርሃም ፡ ስምዖን ፡ ስምዖን ፡ ማርታ ማርታ እንዲል ። እንድም የሥጋ የነፍስ ፈጣሪ ነኝ ሲል ። አንድም ሥጋን ከመቃብር ነፍስን ከገሃነም ሲጠራ ።

፵፬ ወወፅአ ውእቱ ምውት እንዘ ግኑዝ ወእሱር እደዊሁ ወእገሪሁ ።

፵፬ እጁን እግሩን እንደታሰረ ።
ወገጹኒ ጥብሉል በሰበን ።
ፊቱን እንደጠመጠመ ወጣ ።
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ፍትሕዎኬ እንከሰ ወኅድግዎ ይሑር ።
ምትሐት መስሏቸው ነበርና ምትሐት አለመሆኑን ካወቃችሁስ ፈትታችሁ ተውት ይሂድ አንድም እልጸናም መስሏቸው ደግፈውት ነበርና መጽናቱን ካወቃችሁ ፈትታችሁ ተውት ይሂድ አላቸው ።

፵፭ ወብዙኃን እምአይሁድ እለ መጽኡ ኀበ ማርያ ወማርታ ርእዮሙ ዘንተ ተአምረ ዘገብረ እግዚእ ኢየሱስ አምኑ ቦቱ ።

፵፭ ወደማርያና ወደማርታ የመጡ እይሁሁድ ወገን የሚሆኑ ብዙ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን ይኸን ተአምራት አይተው አመኑበት ። ።

፵፮ ወቦ እምውስቴቶሙ እለ ሖሩ ኀበ ፈሪሳውያን ወአስተዋደይዎ ።

፵፮ ከርሳቸው ወገን ወደፈሪሳውያን ሂደው ያሳጡትም አሉ ።
ወነገርዎሙ ኵሎ ተአምረ ዘገብረ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውንም ተአምራት ሁሉ ነገሯቸው ። ሙት አሥነሣ ብለው ።

ዘከመ ተማከሩ አይሁድ ይቅትልዎ ለኢየሱስ ።

፵፯ ወአስተጋብእዎሙ ሊቃነ ካህናት ወፈሪሳውያን ለሕዝብ ።

፵፯ ሊቃነ ካህናት ፈሪሳውያን ሕዝቡን ሰበሰቧቸው ፡
ወይቤልዎሙ ምንተ ንሬሲ ።
ምን እናደርጋለን ምን እናድርግ ።
ናሁ ዝንቱ ብእሲ ብዙኃ ተአምረ ይገብር ።
እነሆ ይህ ሰው ብዙ ተአምራት ያደርግ ጀመር።

፵፰ ወእመኒ ኀደግናሁ ከመዝ ኵሉ የአምን ቦቱ ።

፵፰ እንዲያውም ዝም ብለን ብንተወው ሁሉ ያምንበታል ።

ወይመጽኡ ሰብአ ሮሜ ወይነሥኡ ብሔረነ ወኪያነ ወሕዝበነ ፡
የሮም ሰዎች ተአምራቱን ሲሹ መጥተው ። አንድም ወሬኛ ንጉሥ አነገሣችሁ ብለው ወገናችንን ወገን አገራችንን አገር ያደርጉብናል ።

፵፱ ወይቤሎሙ ፩ዱ እምኔሆሙ ዘስሙ ቀያፋ ሊቀ ካህናት ዘዕብሬቱ ይእቲ ዓመት አንትሙሰ ኢተአምሩ ወኢምንተኒ ። ዮሐ፡ ፲፰፡፲፬ ።

፵፱ ሹመቱ በዚያ ወራት የሚሆን የካህናቱ አለቃ ከነሱ አንዱ ስሙን ቀያፋ የሚሉት እናንተ ምንም ምክር አታውቁም ።

፶ ወኢሂ ትመክሩ ።
፶ አታስቡም ።
ይኄይሰነ ፩ደ ብእሲ ንቅትል ።
አንድ ሰው ብንገድል ይሻለናል ።
ወይሙት ህየንተ ኵሉ እምይትኃጐል ኵሉ ሕዝብ።
ስለ ሕዝቡ ቤዛ ። ሕዝብም ሁሉ በርሱ ምክንያት ከሚጠፋ ።

፶፩ ወዘንተሰ አኮ እምልቡ ዘይቤ ።
፶፩ ይህን የተናገረ ከልቡ አይደለም ማለት በመንፈስ ቅዱስ በታደሰ አእምሮው አይደለም ።
አላ እስመ ሊቀ ካህናት ውእቱ ።
ሊቀ ካህናት ነውና ።
ወዕብሬቱ ይእቲ ዓመት ተነበየ ዘንተ ።
ሹመቱም በዚያ ዓመት ነውና በተአምራት አናገረው እንጂ ዕድግተ በለዓምን እብን ሆሣዕናን እንዳናገረ ። አንድም አኮ እምልቡ ። በአእምሮ ጠባይዕ ዐውቆ አይደለም በሹመቱ አድሮ ያለ ሀብት አናገረው እንጂ በሳኦል አድሮ ሠላሳ ስምንት ዘመን የመንግሥት ሥራ እንደ ሠራ በኃጥእ ቄስ አድሮ ሥጋውን ደሙን እንዲለውጥ። እስመ ሀለዎ ለእግዚእ እየሱስ ይሙት በእንተ ኵሉ ሕዝብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቡ ሁሉ ቤዛ ሁኖ ይሞት ዘንድ አለውና ።

፶፪ ወአኮ በእንተ ሕዝብ ባሕቲቶሙ ።
፶፪ ቤዛነቱ ለሕዝብ ብቻ አይደለም ።
አላ ከመ ያስተጋብኦሙ ለውሉደ እግዚአብሔር እለ ተዘርዉ አሐተኔ ።
በኃጢአት በጣዖት የተበተኑ አሕዛብንም አንድ ያደርጋቸው ዘንድ ነው እንጂ ። ምነው አንድ የሆኑማ በሃይማኖት አይደለምን ቢሉ ሞቱ ያለ ሃይማኖቱ ሃይማኖቱ ያለ ሞቱ አይሆንምና እንዲህ አለ እንጂ አንድ የሆኑስ በሃይማኖት ነው ።

፶፫ ወእምይእቲ ዕለት ተማከሩ ሊቃነ ካህናት ከመ ይቅትልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፶፫ ከዚያ ቀን ጀምሮ ከዚያ ቀን ወዲህ ሊቃነ ካህናት ጌታችንን ሊገሉት መከሩ ።

ዘከመ ተግኅሠ ኢየሱስ እም ኢየሩሳሌም ።

፶፬ ወኢያንሶሰወ እንከ እግዚእ ኢየሱስ ገሃደ ማእከለ አይሁድ

፶፬ ከዚያ ወዲያ ጌታችን ኢየሱስ በአይሁድ ዘንድ ታይቶ አልኖረም ፡
አላ ሖረ ኀበ ሀገር እንተ ትሰመይ ሀገረ ኤፍሬም ቅርብት ለበድው ።
ለምድረ በዳ አቅራቢያ ወደምትሆን የኤፍሬም አገር ወደምትባል ሄደ እንጂ ።
ወነበረ ህየ ምስለ አርዳኢሁ ።
ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ እዚያ ኖረ ፡ ለስቅለት እስኪወጣ ድረስ ከዚያ ይኖራል ።

፶፭ ወቀርበ በዓለ ፋሲካሆሙ ለአይሁድ።

፶፭ አራተኛ ፋሲካ ነው ፡ አይሁድ ፋሲካን የሚያከብሩበት ቀን ደረሰ ።

ወዓርጉ ብዙኃን ሕዝብ ለኢየሩሳሌም እምበሐውርት እምቅድመ በዓለ ፋሲካ ያንጽሑ ርእሶሙ።
ከበዓለ ፋሲካ አስቀድሞ በዓለ አንጽሖን ያደርጉ ዘንድ ብዙ ሰዎች ከየሀገሩ ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ ብፅዓት ያለበት ሰው ሰባት ቀን ከሰው ተለይቶ መሥዋዕት ሠውቶ ማየ ምንዛሕ ተረጭቶ ነውና በዓለ ፋሲካውን የሚያከብር ።

፶፮ ወአኃዙ አይሁድ ይኅሥሥዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፶፮ አይሁድ ጌታን ይሹት ጀመር ።
ወይቤሉ በበይናቲሆሙ እንዘ ይቀውሙ ውስተ ቤተ መቅደስ ምንተ ትብሉ ።
በቤተ መቅደስ ሁነው እርስ በርሳቸው እንዲህ አሉ ።
ናሁ ኢመጽአ ለበዓል ።
ለበዓል ሲመጣ እንይዘዋለን ብለው ነበር ፡ እነሆ ለበዓል አልመጣምሳ ። አንድም በምን ዕዳ በምን ነውር እንይዘዋለን ብለን ነበር ከዚህ የበለጠ ነውር አለ እነሆ ለበዓል አልመጣምሳ አንድም ደግ ነው ትሉት ነበር ደግማ ከሆነ ለበዓል ይመጣ አልነበረምን ለበዓል አልመጣምሳ።
ወአዘዙ ሊቃነ ካህናት ወፈሪሳውያን እምከመ ዘአእመረ ብእሲ ኀበ ሀሎ ይቅጽብዎሙ ከመ የአኃዝዎ ።

ያለበትን ያወቀ ሰው ቢኖር ጠቅሶ ያሲይዛቸው ዘንድ ፈሪሳውያንና ሊቃነ ካህናት ውስጥ ለውስጥ ዐዋጅ ነገሩ ።

በእንተ ድራር ዘቢታንያ ።

ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ ወእምዝ ሖረ እግዚእ ኢየሱስ እምቅድመ ሰዱስ መዋዕል ዘፋሲካ ። ማቴ፡ ፳፮፡ ፮፡ ማር፡ ፲፬፡ ፫ ።

፩ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከበዓለ ፋሲካ ስድስት ቀን አስቀድሞ ሄደ ቅዳሜ አንድም ፋሲካው ከሚውልበት ከስድስተኛው ቀን አስቀድሞ ሄደ ሐሙስ ፡ ሰዱስ ለፍጥረት ወበጽሐ ቢታንያ ኀበ ሀሎ አልዓዛር ዘአንሥአ እምነ ምውታን ።
ከሙታን ለይቶ ያሥነሣው አልዓዛር ካለበት ቢታንያ ደረሰ ።

፪ ወገብሩ ሎቱ ምሳሐ በህየ ።
፪ ከዚያም ግብር አገቡለት ።
ወማርታ ትሜጥዎሙ ።
መፈትፈት ማሳለፍ አይደለም ማርታ እያዘጋጀች አቀረበችላቸው ።
ወአልዓዛር አሐዱ እምእለ ይረፍቁ ምስሌሁ ።
ከጌታ ጋር ተቀምጠው ከሚበሉት አንዱ አልዓዛር ነበር ምትሐት እንዳይደለ ለማጠየቅ ።

፫ ወማርያስ ነሥአት ዕፍረተ ልጥረ ዘናርዱ ጵስጥቂስ ዘዕጹብ ሤጡ ወቀብዓቶ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
፫ ማርያ ግን የደቀቀ የጣፈጠ ሽቱ አምጥታ የጌታን እግሩን ቀባችው ።
ወመዝመዘቶ በሥእርታ ።
በጠጕሯም አደፈችው ።
ወመልአ ቤተ መዓዛሁ ለውእቱ ዕፍረት ።
የሽቱው መዓዛ ቤቱን መላው ሽቱ ሲነካኩት እየተገለጠ ነውና የሚሄድ ፡ አንድም ከመዓዛ መለኮት ጋራ ቢዋሐድ ።
፬ ወይቤ ይሁዳ ስምዖን አስቆሮታዊ ፩ዱ እም፲ቱ ወ፪ቱ አርዳኢሁ ዘሀለዎ ያግብኦ ።
፬ ያሲዘው ዘንድ ያለው ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የአስቆሮት ሰው የሚሆን ይሁዳ እንዲህ አለ ።

፭ ለምንት ኢሤጥዎ ለዝንቱ ዕፍረት ለ፫፻ ዲናር የሀብዎ ለነዳያን ።
፭ ይህን ሽቱ ስድሶች ይመጸውቱት ዘንድ ይትወሀብ ይላል ለነዳያን ይመጸወት ዘንድ ለሦስት መቶ ወቄት ወርቅ ምነው አልሸጡት አለ ።

፮ ወዘንተ ዘይቤ አኮ ዘያጽሕቅዎ ነዳያን ።
፮ ይህን የተናገረ ነዳያን አሳዝነውት አይደለም ምሒረ ነዳያን ይላል የነዳያን ምጽዋት አሳዝኖት አይደለም ።
አላ እስመ ሠራቂ ውእቱ ።
የሰውን ገንዘብ ያነሣሣ ነበርና ወየዓቅብ አስከሬን ጥራን ጠባቂ ነበርና ።
ወቀምጠራ ዘሙዳየ ምጽዋት ሀሎ ውስቶ አዴሁ ።
የሣጥኑ መክፈቻ በእጁ ነበር ።
ወይነሥእ እምዘይትወደይ ውስቴቱ ።
ከገባውም ሁሉ ካሥር አንድ ይወስድ ነበርና ስለ ዚህ ነው እንጂ ።

፯ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ኅድጋ እስመ ፡ ተዓቅቦ ለዕለተ ቀበርየ ።

፯ ጌታም ለምቀበርበት ቀን አስጠብቃዋለችና ተዋት አለው ። ዕለቱን እንዳትቀባው አይሁድ አያስደርሷትም ። በልማዳቸው በሦስተኛው ቀን እንዳትቀባው ፈጥኖ ይነሣባታልና ።

፰ ወነዳያንሰ በኵሉ ጊዜ ሀለው ምስሌክሙ ወዘልፈ ትረከብዎሙ ።

፰ ድኆችስ ዘወትር ከናንተ ጋራ ይኖራሉ ፡ ዘወትር ታገኙዋቸዋላችሁ
ወጊዜ ፈቀድክሙ ታሤንዩ ሎሙ ።
በወደዳችሁ ጊዜ ትሰጧቸዋላችሁ ።
ወኪያየሰ አኮ በኵሉ ጊዜ ዘትረክቡኒ ።
እኔን ግን ዘወትር አታገኙኝም ።

፱ ወብዙኃን እምነ አይሁድ እለ አእመሩ ከመ ሀሎ እግዚእ ኢየሱስ ህየ ወሖሩ ኀቤሁ ።

፱ ከአይሁድም ወገን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚያ እንዳለ ዐውቀው ወደዚያ የሄዱ ብዙ ናቸው ።
ወአኮ በእንተ ኢየሱስ ባሕቲቱ ዘሖረ ።
የሄዱ ጌታችን ኢየሱስን እናያለን ብለው ብቻ አይደለም ።
ዳዕሙ ከመ ይርአይዎ ለአልዓዛርሂ ዘአንሥአ እምውታን ።
ከሙታን ለይቶ ያሥነሣውን አልዓዛርንም ያዩት ዘንድ ነው እንጂ ።

፲ ወተማከሩ ሊቃነ ካህናት ከመ ይቅትልዎ ለአልዓዛር ።
፲ የካህናት አለቆች አልዓዛርን እንግደለው ብለው መከሩ ።
፲፩ እስመ ብዙኃን እምውስተ አይሁድ የሐውሩ በእንቲአሁ ወየአምኑ በእግዚእ ኢየሱስ ።
፲፩ ከአይሁድ ወገኖች አልዓዛርን እናያለን ብለው ሄደው በጌታ የሚያምኑ ብዙ ናቸውና ቢገድሉት ያስነሣባቸው እንጂ የለምን ። ሐተታ ማቴዎስ ረቡዕ ቀባችው ይላል ። ዮሐንስ ቅዳሜ ቀባችው አለ አይጣላም ቢሉ አይጣላም ። ነገር እንደ ዮሐንስ ነው ። ቅዳሚት ቀብታዋለች ማቴዎስ የአሑዱን ሲጽፍ አልፎት ነበርና ከረቡዕ አደረገው

እንጂ ቀቢዩቱም አንዲት ናት ኃጥእት ይላታልሳ ቢሉ ኋላ ተመልሳለች ። ማቴዎስ ራሱን ይላል ዮሐንስ እግሩን አለሳ ቢሉ ከራስ የፈሰሰ እስከ እግር ደረሰ እንዲሉ ። ይህ ፀምን ይታወቃል ቢሉ ተግሣጹን ባለመግደፋቸው ። አንድም እንደ ማቴዎስ በጥንተ ስብከት የፈያታይ ዘየማን እኅት የበላዔ ሰብእ ወገን የምትሆን ማርያም ኃጥእት ይላታል ረቡዕ ራሱን ቀብታዋለች። እንደ ዮሐንስ እኅተ አልዓዛር ቀዳሚት እግሩን ቀብታዋለች ። ተግሣጹንም እንደገደፋት በበረከተ ኀብስት ይታወቃል ።

ዘከመ ገብአ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ።

፲፪ ወበሳኒታ ሰብእ ብዙኃን እለ መጽኡ ለበዓል ሶበ ሰምዑ ከመ ይመጽእ እግዚእ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ።

፲፪ በነጋው ምእሑድ ለበዓል የመጡ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ በሰሙ ጊዜ ።

፲፫ ነሥኡ ፀበርተ ተመርት ዘበቀልት አም ኢየሩሳሌም ወወፅኡ ፍጡነ ሶቤሃ ።

፲፫ የሰሌን ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው ከኢየሩሳሌም ፈጥነው መጡ ።
ወተቀበልዎ እንዘ ይጸርሑ ወይብሉ ሆሣዕና በአርያም ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወንጉሦሙ ለእስራኤል ።
በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ሆሣዕና የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው እያሉ እየጮሁ ተቀበሉት ። በኢየሩሳሌም ሰሌን የለም ወደግብጽ ሲወርድ ከመንገድ አግኝቷት ሂደሽ ደብረ ዘይት ተተከዪ ብሎ አዟት ተነቅላ ሂዳ ተተክላለች ከዚያ ይዘው መጥተዋል ።

፲፬ ወረከበ እግዚእ ኢየሱስ ዕዋለ አድግ ። ዘካ. ፱፥፱ ማቴ፥፳፩ ፱፥፴፰ ።

፲፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አህያ አገኘ። ወተጽእነ ዲቤሃ በከመ ጽሑፍ ተቀመጠባት እንደ ተጻፈ እንዲህ ሲል ።

፲፭ ኢትፍርሂ ወለተ ጽዮን ነዋ ንጉሥኪ ይመጽእ እንዘ ይጼዓን ዲበ ዕዋለ አድግ ።

፲፭ አትፍሪ የጽዮን ልጅ እነሆ ንጉሥሽ ይመጣል ባህያ ግልገል ተቀምጦ ።

፲፮ ወቀዲሙስ ኢያእመሩ አርዳኢሁ ዘንተ ነገረ።
፲፮ አስቀድሞ ግን ደቀ መዛሙርቱ ይህን ነገር አላወቁትም ነበር ።

ዘእንበለ አመ ተሰብሐ እግዚእ ኢየሱስ ።

ጌታ ሳይሰቀል ።
አሜሃ ተዘከሩ ከመ ጽሑፍ ዝንቱ በእንቲአሁ፥
ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ይህ የተጻፈ ስለ እርሱ እንደሆነ ዐወቁት እንጂ ።
ወከመዝ ገብሩ ሎቱ ።
እንዲህ አደረጉለት ።

፲፯ ወስማዕተ ኮንዎ እሙንቱ ሕዝብ እለ ሀለዉ ህየ ምስሌሁ ከመ ጸውዖ ለአልዓዛር እመቃብር ወአንሥኦ እምነ ሙታን ።

፲፯ አልዓዛር አልዓዛር ብሎ ከሙታን ለይቶ እንዳስነሣው ባስነሣው ጊዜ ከርሱ ጋራ የነበሩ ሰዎች መሰከሩለት ።

፲፰ ወበእንተ ዝንቱ ወፅኡ ኵሉ ሕዝብ ወተቀበልዎ ።

፲፰ ስለዚህም ሕዝቡ አመኑበት ።
እስመ ሰምዑ ተአምረ ዘገብረ ።
ያደረገውን ተአምራት ሰምተዋልና ።
ወዘንተሂ መንክረ ።
የሕፃናቱንም ምስጋና አንድም አስመ ሰምዑ ።
ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ያደረገውን ተአምራት ።
ወዘንተሂ መንክረ አልዓዛርን ማስነሣቱን ሰምተዋልና

፲፱ ወይቤሉ ሊቃነ ካህናት ወፈሪሳውያን በበይናቲሆሙ ትሬእዩኑ ከመ አልቦ ዘትበቁዑ ወኢምንተኒ ።

፲፱ ፈሪሳውያን ግን እርስ በርሳቸው የምታገኙት ረብሕ ጥቅም ዘንበቍዕ የምናገኘው ረብሕ ጥቅም እንደሌለ እታውቂም ን ።
ናሁ ኵሉ ዓለም ተለዎ ድኅሬሁ ።
እነሆ ሰው ሁሉ አመነበት አሉ ።

በአንተ አምነቶሙ ለአረሚ ወበእንተ ኢአሚኖቶሙ ለአይሁድ ።

፳ ወቦ እምስብእ ጽርእ አምውስተ አረሚ እለ ዓርጉ ይስግዱ ለበዓል ።
፳ እምሰብአ ጽርእና እምውስተ አረሚ አንድ ወገን በጽርእ ካሉ ካረማውያን ተለይተው ለገቢረ በዓል የወጡ አሉ እስራኤል ከሚጠት በኋላ በየወደዱት አገር ይኖራሉ በሕጋቸው ሁነው ለገቢረ በዓል ይወጣሉ ። አንድም በጽርእ ካሉ ክአረማውያን አም ነው ለገቢረ በዓል የመጡ አሉ ። አንድም በልማድ ይወጡ አሉ የእሥራኤልን በዓል ባያከብሩ በእሥራኤል የታዘዘ መቅሠፍት ያገኛቸው ነበርና ። ሰብአ ጽርእኒ አመ ኢዓርጉ ለበዓል ይግበሩ በዓለ መጸለቶሙ እሙንቱኒ ይትቄሰኩ ዲበ ድቀቶሙ ለእሉ እንዲል ። አንድም ሥነ በዓል ለማየት የወጡ አሉ። ይስግዱ ሲል ያውካል ።

፳፩ ወሐሩ እሙንቱሂ ኀበ ፊልጶስ ዘቤተ ሳይዳ ዘገሊላ ።

፳፩ እርሳቸውም የገሊላ ዕፃ የምትሆን የሳይዳ ሰው ከሚሆን ፊልጶስ ዘንድ ሂደው ።
ወሰአልዎ ወይቤልዎ ንፈቅድ ።
ንርአዮ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ኢየሱስን ልናይ ማለት ልናድርሰት እንወዳለን አሉት

፳፪ ወሖረ ፊልጶስ ወነገሮ ለእንድርያስ ።
፳፪ ፊልጶስም ሂዶ ለእንድርያስ ነገረው ካንድ ሁለት ይሻላል ብሎ እንድም ሰው ማሳደር ለምዷል ብሎ ወሖሩ እንድርያስ ወፊልጶስ ወነገርዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
እንድርያስና ፊልጶስም ሂደው ለጌታ ነገሩት ።

፳፫ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፳፫ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ናሁ በጽሐ ጊዜሁ ከመ ይሰባሕ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
የሰው ልጅ የሚመሰገንበት ጊዜ ማለት የምሞትበት ጊዜ ደረሰ እሞታለሁ እሰቀላለሁ ብላችሁ ሰው እናሳድርልህ ትሉኛላችሁን የሹም ልጅ ኃዘን ቢነግሩት አደን እንዲሉ እንድም ወልደ ዕጓለ እመሕያው እኔም በእምነቴ የምገለጥበት ጊዜ ደረሰ እንግዲህማ ምን እኒህ ብቻ ሁሉ ያምኑብኛል እንጂ ለማለት እንዲህ አለ ።

፳፬ አማን አማን እብለከሙ እመኢወድቀት ኅጠተ ሥርናይ ውስተ ምድር ባሕቲታ ትነብር ።

፳፬ የሥንዴ ቅንጣት ካልተዘራች ካልፈረሰች ካልበሰበሰች ብቻዋን ትኖራለች ።
ወእመሰ ሞተት ብዙኃ ፍሬ ትፈሪ ።
የተዘራች የፈረሰች የበሰበሰች እንደሆነ ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች ፻ ፷ ፴ ። እንድም ኅጠተ ሥርናይ እኔ ካልሞትሁ ብቻዬን በተሐድሶ ጸንቼ እኖራለሁ ። ወእመሰ ሞተት የሞትኩ እንደሆነ ግን ብዙ ምእመናን በተሐድሶ ይኖራሉ ፣ በሚያመጣው ፣ ደሙን በወይን እንደ ሰጠን ለማጠየቅ ራሱን በሐረገ ወይን መስሎ እንደተናገረ ከዚህም ሥጋውን በሥንዴ እንደሰጠን ለማጠየቅ ራሱን በኅጠተ ሥርናይ መስሎ ተናገረ ።

፳፭ ወዘሰ ያፈቅራ ለነፍሱ ለይግድፋ፡ ማቴ፡፲፡ ፴፱ ማር፡፰፡ ፴፭ ሉቃ፡ ፱፡ ፳፬ ።
፳፭ ሰውነቱን ሊያድናት የወደደ በገራኅተ ጥምቀት በገራኅተ መስቀል ይጣላት ።
ወዘሰ ጸልአ ለነፍሱ በዝንቱ ዓለም ።
ነፍሱን የጠላ ማለት ሰውነቱን ለመከራ አሳልፎ የሰጠ ። የዓቅባ ለሕይወት ዘለዓለም ። መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል እንድም በሕይወት ዘለዓለም በክብር ይከባከባታል ።

፳፮ ወእመቦ ዘይትለአከኒ ሊተ ለይትልወኒ ።
፳፮ በሃይማኖት የሚያገለግለኝ ሰው ቢኖር በምግባር ይምሰለኝ ።

እስመ ኀበ ሀሎኩ አነ ህየ ይሄሉ ዘይትለአከኒ ።
በሃይማኖት የሚያገለግለኝ እኔ ከገባሁበት ገብቶ ይኖራልና ። እንድም በሃይማኖት በምግባር የሚገለግለኝ ሰው ቢኖር እኔ በተሰቀልኩባት መስቀል ተሰቅሎ እኔ በሞትኩበት ሞት ሞቶ በመከራ ይምሰለኝ ።
እስመ ኀበ ሀሎኩ በሃይማኖት በምግባር የሚያገለግለኝ እኔ በተሰቀልኩባት መስቀል ተሰቅሎ እኔ በሞትኩባት ሞት ሙቶ እኔ ከገባሁበት ውሳጤ መንጦላዕት ገብቶ ይኖራልና ።
ወዘሊተ ተልእከኒ ያከብሮ አቡየ ።
እኔን ያገለገለኝን አባቴ ያከብረዋል ማለት እኔን ባገለገለኝ አባቴ ያድርበታል ።

፳፯ ወይእዜሰ ተሀውከተኒ ነፍስየ ።
፳፯ ዛሬስ ሰውነቴ ሁከት ሥጋዊ ታወከችብኝ ወምንተ እብል ።
ምን እላለሁ ።
አባ አድኅና ለነፍስየ እምዛቲ ሰዓት ።
አባቴ ከዚህች ሰዓት ሰውነቴን አድናት እላለሁ እንጂ ሌላ ምን እላለሁ ።
ወባሕቱ በእንተ ዝንቱ መጻእኩ ።
ነገር ግን ስለዚህ ሰው ሁኛለሁ ፤
ወበጻሕክዋ ለዛቲ ሰዓት ።
ከጊዜውም ደርሻለሁ ። እንድም ወይእዜሰ ብለህ መልስ ። ሰውነቴ ሁከት መንፈሳዊ ታወከችብኝ አድርጋት እትተዋት የሚል ሁከት ተነሣሣችብኝ ወምንተ እብል አባቴ ሰውነቴን ከዚህ ሰዓት አድናት እላለሁን አልልም ። ወባሕቱ አድናትስ እንዳልል አድናትም እንዳልል ስለዚህ ሰው ሁኛለሁ ከጊዜውም ደርሻለሁ ።

፳፰ አባ ሰብሖ ለወልድከ ።
፳፰ አባቴ ሆይ ልጅህን ግለጸው ።
ወመጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ሰባሕኩከሂ ።
በዮርዳኖስ በደብረ ታቦር ገለጽኩህ ።
ወዓዲ እሴብሐከ ።
ዳግመኛም ሁለተኛ በመስቀል በተአምራት እገልጽሃለሁ የሚል ቃል ተሰማ ።

፳፱ ወሕዝብሰ እለ ይቀውሙ ወይሰምዑ ይቤሉ ነጐድጓድ ውእቱ ።
፳፱ ርቀው ቆመው የሚሰሙት ሕዝብ ግን ነጐድጓድ ነው አሉ ።
ወቦ እለ ይቤሉ መልአክ ተናገሮ ።
ቀርበው የነበሩ መልአክ ተናገረው ያሉም አሉ ። እንድም ፍሬ ነገሩን ያልሰሙት ነጐድጓድ ነው አሉ ። ፍሬ ነገሩን የሰሙት መልአክ ነው አሉ ።

፴ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ አኮ በእንቲአየ ዘመጽአ ዝቃል ።

፴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህ ቃል የተሰማ ስለኔ አይደለም ።
አላ በእንቲአክሙ ።
ስለናንተ ነው እንጂ ብሎ መለሰላቸው ።

፴፩ ወናሁ አብለክሙ ይእዜ በጽሐ ኵነኔሁ ለዝንቱ ዓለም ።

፴፩ የዚህ ዓለም ፍርድ ደረሰ ማለት የዚህ ዓለም አበጋዝ ዲያብሎስ ድል የሚነሣበት ጊዜ ደረሰ ብዬ እነግራችኋለሁ ።
ወ እምይእዜሰ ይሰድድዎ ለመለአኬ ዝንቱ ዓለም።
እንግዲህ ወዲህስ የዚህ ዓለም አበጋዝ የሚሆን ዲያብሎስን ድል ይነሡታል ።
ወያወፅእዎ አፍአ ።
ከማደሪያው ከሰው ልቡና አስወጥተው ይሰዱታል ቦታውን መልቀቁ ድል መነሣቱ ነውና አንድም በጽሐ ኵነኔሁ ብለህ መልስ ሰው ሁሉ አንድ ወገን ሁኖ የሚገዛበት ጊዜ ደረሰ ያወፅእዎ አፍአ አይለወጥም

፴፪ ወአነኒ አምከመ ተለዓልኩ እምድር እስ ሕዝብ ኵሉ ኀቤየ።

፴፪ እኔም ከምድር ከፍ ብዬ የተሰቀልኩ እንደሆነ ሰውን ሁሉ በግብርም በክብርም ወደኔ እቀርበዋለሁ ።

፴፫ ወዘንተ ዘይቤ እንዘ ይህምሮሙ በአይ ሞት ሀለዎ ይሙት

፴፫ ይህን የተናገረ በምን ሞት ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያስረዳ ነው ። አንድም በምን ሞት ይሞት ዘንድ አለው ቢሉ በመሰቀል ተሰቅሎ ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያስረዳ ።
ይህን ተናገረ ። እምከመ ተለዓልኩ አለ ።

፴፬ ወአውሥእዎ ሕዝብ ።

፴፬ ሕዝቡም መለሱ ። መዝ፡፻፱፡፬ ኢሳ፡ ፱፡፯ ሕዝ፡፴፯፡፳፭ ።
ወይቤልዎ ንሕነሰ ሰማዕነ በውስተ ኦሪት ከመ ለዓለም ይነብር ክርስቶስ ።
እኛስ በክርስቶስ ሞት እንደሌለበት በኦሪት ሰምተን ነበር ሰምተናል ።
ወእፎ እንከ ትብለነ አንተ ሀለዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ይትለዓል ።
አንተ የሰው ልጅ ክርስቶስ ይሰቀል ዘንድ አለው እንደምን ትላለህ አሉት ። ወርኢኩ በራእየ ሌሊት ወመጽአ ከመ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ወበጽሐ ኀበ ብሉየ መዋዕል ወተውህበ ሎቱ መንግሥት ወምኵናን መንግሥቱኒ መንግሥት ዘለ ዓለም ወምኵናኑኒ ለትውልደ ትውልድ ወአልቦ ማሕለቅት ለመንግሥቱ ። ያለውን ለውጦ አነበበው ፡ ይህንማ የተናገረ ዳንኤል አይደለምን ስለ ምን ኦሪት አለው ቢሉ መጻሕፍተ ሐዲሳትን በመከብባቸው ወንጌል እንዳላቸው መጻሕፍተ ብሉያትንም በመከብባቸው ኦሪት ይላቸዋልና ። አኮኑ ውስተ ኦሪትክሙ ጽሑፍ አንሰ እቤ አማልክት አንትሙ እንዳለ ዳዊትን ኦሪት ብሎ ። ወበውስተ ኦሪትኒ ይብል በካልዕ ልሳን ወበካልዕ ከናፍር እትናገሮሙ ለሕዝብ እንዳለ ኢሳይያስን ኦሪት ብሎ ከዚህም ዳንኤልን ኦሪት ብሎ እንዲህ አለ ።
መኑ እንከ ዝንቱ ወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
ይህ የሰው ልጅ ክርስቶስ ማነው አሉት ።

፴፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ዓዲ ኅዳጠ መዋዕለ ሀሎኩ ምስሌክሙ ብርሃን ።

፴፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ብርሃን እኔ ጥቂት ቀን ከናንተ ጋራ እኖራለሁ ።
እንሶሰዉ እንዘ ብክሙ ብርሃን ዘእንበለ ይርከብክሙ ጽልመት ።
ብርሃን ሳለ ሳይጨልም ተመላለሱ ማለት እኔ ሳለሁ በኔ እመኑ ።
እስመ ዘየሐውር ውስተ ጽልመት ኢየአምር ኀበ የሐውር ።
በጨለማ የሚሄድ የሚሄድበትን አያውቀውምና ማለት እኔ ከሞትኩ በኋላ እኔ የምሠራውን ሥራ ሠርቶ በኔ ማሳመን የሚቻለው የለምና ።

፴፮ አምጣነ እንዘ ብክሙ ብርሃን እመኑ በብርሃን ።
ብርሃን ሳለሁ በኔ እመኑ ።
ከመ ትኩኑ ውሉደ ብርሃን ።

፴፮ ዕውቀት ያላችሁ ልጆች ትባሉ ዘንድ አንድም አምጣነ እንዘ ብክሙ ብለህ መልስ ። ብርሃን ዕድሜያችሁ ሳለ በኔ እመኑ ከመ ትኩኑ ውሉደ ብርሃን ዕውቀት ያላችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ አንድም የእኔ ልጆች ትባሉ ዘንድ ።
ወዘንተ ብሂሎ እግዚእ ኢየሱስ ሖረ ወተኃብአሙ።
ይህን ተናግሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰውሯቸው ሄደ ጊዜው የተከሥቶ ሲሆን ረቂቅ መለኮት እንደሆነ ረቂቅ መለኮትን እንደ ተዋሐደ ለማጠየቅ።

፴፯ ወእንዘ መጠነዝ ተአምረ ይገብር በቅድሜሆሙ ኢአምኑ ቦቱ ።

፴፯ በፊታቸው ይህነን ያህል ተአምራት ሲያደርግ አላመኑበትም ።

፴፰ ከመ ይብጻሕ ቃለ ኢሳይያስ ነቢይ ዘይቤ እግዚኦ መኑ የእምነነ ሰምዐነ ።

፴፰ አቤቱ ትምህርታችንን ማን ይቀበለናል ። ወለመኑ ተከሥተ መዝራዕቱ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር እብ ቢሉ መዝራዕቱ ወልድ እግዚአብሔር ወልድ ቢሉ መዝዕራቱ ሥልጣኑ ለማን ተገለጠ ብሎ ኢሳይያስ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ።

፴፱ ወበእንተ ዝንቱ ስእኑ አሚነ ።
፴፱ ስለዚህ ማመን ተሳናቸው ።
እስመ ካዕበ ይቤ ኢሳይያስ ዳግመኛ ኢሳይያስ እንዲህ ብሏልና ።

፵ ዖራ አዕይንቲሆሙ ።
፵ ዓይናቸው ታውሯል ።
ወገዘፋ አልባቢሆሙ ልባቸው ደንድኑዋልና ።
ከመ ኢይርአዩ በአዕይንቲሆሙ ።
ባይናቸው እንዳያዩ ።
ወኢይለብው በአልባቢሆሙ ።
በልቦናቸውም እንዳያውቁ ።
ከመ ኢይትመየጡ ኀቤየ ።
ወደኔ እንዳይመለሱ ፤
ወኢይሣሃሎሙ ።
ይቅር እንዳልላቸው ።

፵፩ ወዘንተ ይቤ ኢሳይያስ እስመ ርእየ ስብሐተ እግዚአብሔር ወነገረ በእንቲአሁ ፤

፵፩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ጌትነቱን እውቋልና ከሰው ሹመት ሽልማት ሳይሻ ዖራ ገዘፋ ብሎ ደፍሮ ተናገረ ። አንድም እግዚአብሔር የሚያወርሰውን ክብር ዐውቋልና በመስቀል ይሰቀሉኝ በመጋዝ ይተርትሩኝ ብሎ ሳይፈር ሳያፍር ደፍሮ እንዲህ ብሎ የርሱን ነገር ተናገረ ።

፵፪ ወብዙኃን እመላእክተ ሕዝብ እለ አምኑ ቦቱ ።

፵፪ ከሕዝብም አለቆች ወገን ያመኑበት ብዙ ናቸው ።
ወባሕቱ ኢያግሐዱ በእንተ ፍርሃቶሙ ለፈሪሳውያን።
ነገር ግን ፈሪሳውያንን ስለ ፈሩ እምነታቸውን እልገለጡትም ።

ከመ ኢይስድድዎሙ እምኩራብ ።
ከምኵራብ እስወጥተው እንዳይሰዷቸው ።

፵፫ እስመ አብደሩ ስብሐተ ሰብእ እምስብሐተ እግዚአብሔር

፵፫ እግዚአብሔር ከሚያወርሳቸው ክብር ይልቅ ውዳሴ ከንቱን ከመንግሥተ ሰማይ ምኩራብን ከወንጌል አሪትን ወደዋልና ።

፵፬ ወጸርሐ እግዚእ ኢየሱስ በዓቢይ ቃል።
፵፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጮሆ እስምቶ ተናገረ ።
ወይቤ ዘየአምን ብየ አኮ ብየ ኪያየ ባሕቲቶ ዘየአምን ።
በኔ ያመነ በኔ ብቻ አላመነም ።
ዘእንበለ በአብ ዘፈነወኒ ፤
በላከኝ በአባቴ አመነ እንጂ ።

፵፭ ወዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለዘፈነወኒ ።
፵፭ እኔን ያየ አባቴን አየ ።

፵፮ ወአንሰ ብርሃን መጻእኩ ውስተ ዓለም ።
፵፮ ብርሃን እኔ በመምህርነት ወደዚህ ዓለም መጣሁ ሰው ሆንሁ ።

ከመ ኵሉ ዘየአምን ብየ ኢይንበር ውስተጽልመት።
በኔ ያመነ ሁሉ በክሕደት በገሃነም እንዳይኖር።

፵፯ ወዘኒ ሰምዓ ቃልየ ወኢዓቀቦ አኮ አነ ዘእኴንኖ ።

፵፯ የኔን ቃል ሰምቶ በኔ ባላመነ እኔ አልፈርድበትም ።
እስመ ኢመጻእኩ ከመ እኴንኖ ለዓለም ።
አድነው ዘንድ ነው እንጂ ልፈርድበት አልመጣሁምና ።

፵፰ ወዘሰ ከሐደኒ ።
፵፰ እኔን በካደ ።
ወኢተወከፈ ቃልየ ።
ትምህርቴን ባልተቀበለኝ ግን ።
ሀሎ ዘይኴንኖ ።
የሚፈርድበት አለ ።
ቃል ዘአነ ነበብኩ ውእቱ ይኴንኖ በደኃሪት ዕለት።
አሁን የምናገረው ነገር በኋለኛዪቱ ቀን ይፈርድበታል ።

፵፱ እስመ አኮ ዘእምኀቤየ ነበብኩ ።
፵፱ የማስተምር ከራሴ አንቅቼ አንድም ከራሴ ብቻ እንቅቼ አይደለምና ።
አላ እብ ዘፈነወኒ ውእቱ ትእዛዘ ወሀበኒ ዘከመ እነብብ ወዘከመ ዕብል ።
የምናገረውን የማስተምረውን እንደምናገር እንደማስተማር የላከኝ አባቴ ትእዛዙን ነገረኝ እንጂ ።

፶ ወአአምር ከመ ትእዛዙ ሕይወት ውእቱ ዘለዓለም ።

፶ ትእዛዙም የዘለዓለም ሕይወት እንደሆነች ዐውቃለሁ ።
ወዘሂ እነግር አነ በከመ ይቤለኒ አብ ከማሁ እነግር ።

የማስተምረውንም ከአብ በሀልውና ያገኘሁትን አስተምራለሁ ። አባቴ ሙት ተሰቀል እንዳለኝ ሙቱ ተሰቀሉ እላለሁ ።

በእንተ ተፍጻሜ ድራር ወኅፅበተ
እገሪሆሙ ለሐዋርያት ።

ምዕራፍ ፲፫ ።

፩ ወእምቅድመ በዓለ ፋሲካ ኮነ የአምር እግዚእ ኢየሱስ ከመ በጽሐ ጊዜሁ ከመ ይፍልስ እምዝንቱ ዓለም ወየሐውር ኀበ አብ ዘፈነዎ ። ማቴ፡፳፮፡፪ ፡ ማር፡፲፬፡፩ ። ሉቃ፡ ፳፪፡፩ ።

፩ ከበዓለ ፋሲካ አስቀድሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ አብ እንዲሄድ ጊዜው እንደደረሰ ያውቅ ነበር ። አፍቀሮሙ ማንኛ ።
እንድም ሶበ ኮነ የአምር ከመ ይፍልስ ፡ ከበዓለ ፋሲካ አስቀድሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ አብ ይሄድ ዘንድ ጊዜው እንደ ደረሰ ያውቅ በነበረ ጊዜ ።
አፍቀሮሙ ለእሊኣሁ እለ ውስተ ዓለም ።
ወገኖቹን በዓለም ያሉትን ወደዳቸው ፡ ደቀ መዛሙርቱን እግራቸውን አጠባቸው ።
ወለዝሉፉ አፍቀሮሙ ።
ፈጽሞ ወደዳቸው ማለት ሥጋውን ደሙን ሰጣቸው ። እንድም አፍቀሮሙ እሰቀልላችኋለሁ አላቸው ። ወለዝሉፉ አፍቀሮሙ ልጅነትን እሰጣችኋለሁ አላቸው ።

፪ ወእንዘ ይዴረሩ ቦአ ሰይጣን ውስተ ልቡ ለይሁዳ ስምዖን አስቆሮታዊ ከመ ያግብኦ ።

፪ ሲበሉ ያሲዘው ዘንድ የአስቆሮት ሰው በሚሆን በይሁዳ ሰይጣን አደረበት ። ተለይቶትን ያውቃል አስፈጻመው ለማለት ነው እንጂ ።

፫ ወሶበ ኮነ የአምር እግዚእ ኢየሱስ ከመ ኵሉ ተውህቦ እምኀበ አብ ወከመ አወፈዮ አብ ኵሎ ውስተ እዴሁ ።

፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብ ሁሉን በእጁ ጭብጥ በእግሩ እርግጥ አድርጎ እንዳስገዛለት ያውቅ ነበር ፡ ያውቅ በነበረ ጊዜ ።
ወከመ እምኀበ እግዚአብሔር ወፅአ ።
ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣ ፡
ወኀበ እግዚአብሔር የሐውር ።
ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ ያውቅ ነበር ያውቅ በነበረ ጊዜ ።

፬ ወተንሥአ እምኀበ ይዴረሩ ወእንበረ አልባሲሁ ።

፬ እያሠሩ የመጡ እንደሆነ ወተንሥአ በንይዞ የመጡ እንደሆነ ከሚመገቡበት ተነሥቶ ልብሱን አኖረ ። ወነሥአ መክፈ ዘለንጽ ወቀነተ ሐቌሁ ። ዘርፍ ያላት ዝናር እንሥቶ ወገቡን ታጠቀ ሥራ የምታሠራ የምታስጌጥ ናት ። ኢዮአብ ወደ ሠልፍ ሲገባ እየለበሳት ይገባ እንደ ነበረች ያለች ናት ብሰ መንድያ ይላታል በሺህ ዘሐ የተሠራች ናት አንቀልባፊዶ ማጠቆ ገልድ ጕለቫ ይላታል ።

፭ ወወደየ ማየ ውስተ ንብቲራ ።
፭ ውኃ በኵስኵት ቀዳ ።
ወአኀዘ ይሕፅብ እገሪሆሙ ለአርዳኢሁ ።
የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጥብ ጀመር ።
ወመዝመዘ በውእቱ መክፈ ዘቀነተ ።
በታጠቀበት ዘርፍ ባለው ዝናር እያበሰ ያደርቅ ጀመር ።

፮ ወበጽሐ ኀበ ስምዖን ጴጥሮስ
፮ ከጴጥሮስ ደረሰ ።
ወይቤሎ አንተኑ እግዚኦ ተሐፅበኒ እገርየ ።
አቤቱ አንተ እግሬን ታጥበኛለህን ፣ ዘተሐፅበኒ እግሬን የምታጥበኝ አንተን ነህ አለው ።
፯ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፯ ጌታም መለሰ ።

ወይቤሎ ዘእገብር አነ አንተ ኢተአምር ይእዜ ።
እኔ ዛሬ የምሠራውን አንተ አታውቅም አለው ።
ወባሕቱ ድኅረሰ ተአምሮ ።
ኋላ ግን ታውቀዋለህ ነገር ግን ኋላ ታውቀዋለህ ።

፰ ወይቤሎ ስምዖን ጴጥሮስ ኢተሐፅበኒ እገርየ ለዓለም ።

፰ ቊርጽ አድርጎ አንተ እግሬን አታፅበኝም ኢትሕፅበኒ አትፅበኝ አለው ። ሕፅበት በይሁዳ ይጀመራል ልቡ በፍቅረ ንዋይ ተታኗልና ዝም ብሎ ይታፀባል ፣ ከጴጥሮስ ይደርሳል ይከራከራል ይረታል ይታፀባል ፡ እንድም በጴጥሮስ ይጀምራል ይከራከራል ይረታል ይታፀባል ዓሥራ እንዱ እርሱን አብነት አድርገው ይታፀባሉ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ አማን እማን እብለከ ከመ ኢሐፀብኩከ እገሪከ አልብከ ክፍል ምስሌየ ።
እኔ ካላፀብኩህ ከኔ ጋራ አንድነት የለህም ብዬ እንደሌለህ በውነት እነግርሃለሁ ።

፱ ወይቤሎ ጴጥሮስ አኮ እገርየ ባሕቲቶ ዘተሐፅበኒ ።

፱ ካንተ ጋራ አንድነትስ ከሚቀርብኝ እግሬን ብቻ አታፅበኝም የምታፅበኝ እግሬን ብቻ አይደለም ።
ወዓዲ እደውየኒ ወርእስየኒ ።
እጆንም ራሴንም ነው እንጂ አለው ።

፲ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ዘሰ ወፅአ ተሐፅበ ኢይፈቅድ ይትሐፀብ ዘእንበለ እገሪሁ ዳዕሙ ።

፲ ፈጽሞ የታጠበ እግሩን ብቻ ነው እንጂ ሌላውን አካሉን ሊታጠብ አይሻም ።
እስመ ንጹሕ ኵለንታሁ ።
ሌላው አካሉ ንጹሕ ነውና ።
ወአንትሙሰ ንጹሓን አንትሙ
እናንተ ግን ንጹሓን ናችሁ ።
ወባሕቱ አኮ ኵልክሙ ንጹሓን ።
ነገር ግን ንጹሓን ማለቴ ለሁላችሁ አይደለም ።

፲፩ እስመ የአምር እግዚእ ኢየሱስ ዘያገብእ ወበእንተ ዝንቱ ይቤ አኮ ኵልክሙ ንጹሓን ።

፲፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያሲዘው ይሁዳ እንደሆነ ያውቃልና ስለዚህ ሁላችሁ ንጹሓን አይደላችሁም አለ ።

፲፪ ወሶበ ሐፀቦሙ እገሪሆሙ ነሥአ አልባሲሁ ወረፈቀ ካዕበ ምስሌሆሙ ።

፲፪ እግራቸውን ካጠባቸው በኋላ ልብሱን አንሥቶ ሁለተኛ ከርሳቸው ጋራ ተቀመጠ ከዚህ በፊት ነቢብን አስቀድሞ ገቢርን ያስከትልላቸው ነበር ዛሬ ግን ገቢርን አስቀድሞ በነቢብ ለማስተማር ተቀመጠ የታጠቀበትን ለዮሐንስ ወንጌላዊ ሰጥቶታል ጌታ በታጠቀበት ቢታጠቅ ሕገ ሥጋ ጠፍቶለታል ፍቁረ እግዚእ ያሰኘውም ይህ ነው ።
ወይቤሎሙ አእመርክሙኑ ዘገበርኩ ለክሙ አነ ።
ያደረግሁላችሁን ዐወቃችሁትን አላቸው ።

፲፫ አንትሙሰ ትብሉኒ ሊቅነ ወእግዚእነ ።

፲፫ እናንተ መምህራችን ጌታችን ትሉኛላችሁ።
ወሠናየ ትብሉ ።
መልካም ተናግራችኋል ።
እስመ ከማሁ አነ ሊቅክሙ ወእግዚእክሙ ።
መምህራችን ጌታችን እንዳላችሁኝ መምህራችሁ ጌታችሁ ነኝና ።

፲፬ ወሶበ አነ እንዘ ሊቅክሙ ወእግዚእክሙ ሐፀብኩክሙ እገሪክሙ ።

፲፬ እኔ መምህራችሁ ጌታችሁ ስሆን እግራችሁን ካጠብኳችሁ ።
አንትሙኒ ይደልወክሙ ትሕፅቡ እግረ ቢጽክሙ ።
እናንተም የወንድማችሁን እግር ልታጥቡ ይገባችኋል ።

፲፭ እስመ አርአያየ ወሀብኩክሙ
፲፭ አብነት ሁኛችኋለሁና ።
ከመ ትግበሩ አንትሙኒ ለቢጽክሙ በከመ ገበርኩ ለክሙ አነ ።
እናንተም እኔ እንዳደረግሁላችሁ ታደርጉ ዘንድ ይህንም መጻሕፍት ትሕትና ብለው ወስደውታል ትርጓሜ ወንጌል አዘርዕ ፍቅረ ወትሕትና ውስተ አልባቢክሙ ብሎ ሊቁም ከመ ያርትዕ አእጋረ ሕዝብ በፍቅረ ትሕትና ብሎ ፡ ሠለስቱ ምእትም በሕንጻ መነኮሳት ኢትትሐከይ ሐፂበ እግረ አኀውሶበ መጽኡ ኀቤከ እስመ በእንተ ዛቲ ግብር ይትኃሠሥ ምሙ ለእለ ያጸርእዋ እመኒ ኮኑ ኤጲስቆጶሳተ እስመ እግዚእነ ሐፀበ እግረ አርዳኢሁ ፡ ወይቤሎሙ በከመ ገበርኩ ለክሙ አነ ከማሁ አንትሙኒ ይደልወክሙ ትሕፅቡ እግረ ቢጽክሙ እስመ አርአያየ ወሀብኩክሙ ብለዋል ፊልክስዩስም ወሕፅበተ ፋሲካ ትትሜሰል በምሥጢረ ትሕትና ፍጽምት ብሏል ።

፲፮ አማን አማን እብለክሙ አልቦ ገብር ዘየዐቢ እምእግዚኡ ወአልቦ ሐዋርያ ዘየዓቢ እምዘፈነዎ ። ማቴ.፲፥ ፳፬ ሉቃ. ፮፥ ፵ ዮሐ፥፲፭፥ ፳ ።

፲፮ በዚያውም ላይ ከጌታው የሚበልጥ ባሪያ ከላኪው የሚበልጥ መላክተኛ የለም ።

፲፯ ወእመሰ ዘንተ ተአምሩ ብፁዓን አንትሙ እመ ገበርክምዎ ።

፲፯ ይኽን ዐውቃችሁ ብትሠሩት ንዑዳን ክቡራን ናችሁ ። ዓሥረኛውን ብፁዓን በዮሐንስ ያመጣዋል ያልነው ይህ ነው ።

፲፰ ወኢኮ በእንተ ኵልክሙ ዘእብል ዘንተ።
፲፰ ይህን የምናገር ስለ ሁላችሁ አይደለም።
እስመ አነ አአምር መኑ እሙንቱ አለ ኀረይኩ ።
የመረጥኳችሁ እነማንም እንደሆናችሁ ዓውቃለሁና።
ወባሕቱ ከመ ይብጻሕ ቃለ መጽሐፍ ዘይቤ ዘይሴሰይ እክልየ አንሥአ ሰኰናሁ ላዕሌየ ።
ባሕቱ ዋዌ ነው ። መጽሐፍ እንዲህ ብሎ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ የመረጥኳችሁ እነማንም እንደሆናችሁ ዐውቃለሁና ። አንድም መጽሐፍ እንዲህ ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ እህሌን የሚመገብ አንድም እህል ትምህርቴን የሚመገብ ይሁዳ ሰኰናውን አነሣብኝ ወፅአ በሌሊት የሚል ነው ።

፲፱ ወይእዜሰ እነግረክሙ ዘእንበለ ይኩን ።
፲፱ ዛሬ ግን አስቀድሞ ነገርኳችሁ ።
ከመ እመ ኮነ ትእመኑ አንትሙ ከመ አነ ውእቱ ።
እኔ እንደሆንኩ ማለት በተደረገ ጊዜ የባሕርይ አምላክ እንደሆንኩ ታምኑ ዘንድ አስቀድሞ ዐውቆ እንጂ ነው የነገረን የባሕርይ አምላክ እንጂ ቢሆን ብላችሁ ። ማቴ፥፲፥ ፵ ሉቃ፥ ፲፮ ።

፳ አማን አማን እብለክሙ ዘተወክፎ ዘፈነውኩ አነ ኪያየ ተወክፈ ።

፳ የላክሁትን የተቀበለ እኔን ተቀበለ እኔን በተቀበለ ማለት የላክሁትን በተቀበለ እድርበታለሁ ወዘኪያየ ተወክፈ ተወክፎ ለዘፈነወኒ ።

እኔን የተቀበለ አባቴን ተቀበለ እኔ ባደርኩበት አባቴ ያድርበታል ።

ዘከመ አእመረ እግዚእ ኢየሱስ ዘያገብእ ።

፳፩ ወዘንተ ብሂሎ እግዚእ ኢየሱስ ተሀውከ በመንፈሱ። ማቴ፡፳፮፡፳፩ ማር፡፲፬ ፡ ፲፰ ሉቃ፡፳፪፡፳፩።

፳፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ተናግሮ በልቡ አዘነ ።
ወስምዐ ኮነ ወይቤ አማን አማን እብለክሙ ከመ አሐዱ እምኔክሙ ያገብአኒ ።
ከናንተ አንዱ እንዲያስይዘኝ ያስይዘኛል ብዬ በውነት እነግራችኋለሁ ብሎ መሰከረ ።

፳፪ ወተናጸሩ አርዳኢሁ በበይናቲሆሙ ።

፳፪ ደቀ መዛሙርቱም እርስ በርሳቸው ተጠቃቀሱ ።
እስመ ኢያእመሩ ወኃጥኡ እንበይነ መኑ ይብል ዘንተ ።
ይህን የተናገረ ስለማንም እንደሆነ ዐላወቁምና ።

፳፫ ወሀሎ አሐዱ እምአርዳኢሁ ዘይረፍቅ ውስተ ሕፅኑ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፳፫ የጌታ ባለሟል የሚሆን ከደቀ መዛሙርቱ አንድ ሰው ነበር ።
ወያፈቅሮ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታም ይወደዋል ።

፳፬ ወቀጸቦ ስምዖን ጴጥሮስ ሎቱ ወይቤሎ ተስአል በበይነ መኑ ይብል ዘንተ ።

፳፬ ይህን የተናገረ ስለ ማንም እንደሆነ ቀርበህ ጠይቀው አለው ።

፳፭ ወረፈቀ ውእቱ ረድእ ዲበ እንግድአሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፳፭ ያም ባለሟሉ በጌታችን እጠገብ ተቀመጠ።
ወይቤሎ እግዚእ መኑ ውእቱ ዘያገብአከ ።
እቤቱ የሚያሲዝህ ማነው አለው ።

፳፮ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ዝውእቱ ዘአነ እጸብሕ ሎቱ ኅብስተ ወእሜጥዎ ውእቱ ዘያገብአኒ ።

፳፮ እንጀራ በወጥ ጠልቄ የምሰጠው እሱ ያሲዘኛል አለው ።
ወጸብሐ ኅብስተ ወመጠዎ ለይሁዳ ስምዖን አስቆሮታዊ ።
እንጀራ በወጥ ጠልቆ የአስቆሮት ሰው ለሚሆን ለይሁዳ ሰጠው ።

፳፯ ወእምድኅረ ውእቱ ኅብስት ወሀቦ ኅብስተ

፳፯ ለሐዋርያት ሥጋውን ከሰጣቸው በኋላ ወደ ኅብስትነት ለውጦ ሰጠው ፤ ፍትሐተ ማይ እንዳለ ፍትሐተ ማይስ በሀገራችን ነው እንጂ በሀገራቸው የለም ። ማየ ኅቦን ከሆነ በኋላ ማየ መቍረርን አይሆንም እርሱስ ዳቦ ቢበላ ፍዳ ያመጣበታልን ብሎ በማዓ ፋሲካውን ከበሉ በኋላ ሥጋውን ሰጠው
ወምስለ ውእቱ ኅብስት ቦአ ሰይጣን ውስተ ልቡ ለይሁዳ በሥጋው ምክንያት ሰይጣን አደረበት ፤ ሥጋው ደሙ ሰይጣን ያርቃል እንጂ ሰይጣን ያሳድራልን ቢሉ ፍዳ የሚያመጣበት ነውና ፤ ሆድ ቁርጠት ታማሚ ነጭ በመረቅ በበላ ጊዜ ደዌው እንዲቀሰቀስበት ።
ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ዘትገብር እንከ ፍጡነ ግበር ።
የምትሠራውን ፈጥነህ ሥራ አለው ።

፳፰ ወኢያእመሩ እለ ይረፍቁ ምስሌሁ ከመ በእንተ ምንት ይቤሎ ዘንተ ።

፳፰ ተቀምጠው ያሉት ይህን ያለው ለምንም እንደሆነ ዐላወቁም ።

፳፱ ወቦ እለ መሰሎሙ ከመ በእንተ አስከሬን ዘሙዳየ ምጽዋት ዘሀሎ በኀበ ይሁዳ ዘይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ሑር ተሣየጥ ዘንገብር ለበዓል።

፳፱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ ዘንድ ስላለው ጥሬን ለበዓል የምናደርገው ።
እው ዘንሁብ ለነዳያን ።
ወይም የምንመጸውተው ዋጋ አድርግ ያለው የመሰላቸው አሉ ።
እስመ ውእቱ የዓቅብ አስከሬነ ቀምጠራ ዘሙዳየ ምጽዋት ።

መከፈቻ ያለው ሳጥን ጠባቂ ነበርና ።
ወቀምጠራ ዘሙዳየ ምጽዋት ሀሎ ውስተ እዴሁ ።
የሳጥን መከፈቻም በጁ ነበርና ።

፴ ወተመጢዎ ይሁዳ ውእተ ኅብስተ ወፅአ በሌሊት ።

፴ ይሁዳም ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ እንደ ጽኑ ጠላት በሌሊት ወጥቶ ሄደ ።

ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ እምድኅረ ድራር ወዘከመ ተነበየ ኅዲጎተ ዘሐዋርያት ።

፴፩ ወወፂአ ውስተ ጊዜ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ይእዜኬ እንከ ተሰብሐ ወልደ ዕጓለ እመሕያው

፴፩ እርሱ ወጥቶ ከሄደ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ ተመስገነ ተገለጠ እላ

ቸው በዮርዳኖስ ።
ወእግ ዚአብሔርኒ ተሰብሐ ቦቱ ።
እግዚአብሔርም ተመሰገነበት ተገለጸበት ፤ በደብረ ታቦር ።

፴፪ ወእመሰ እግዚአብሔር ተሰብሐ ቦቱ ።
፴፪ እጸፋውን ተናገረ እግዚአብሔርም ከተመሰገነበት ከተገለጸበት ።
እግዚአብሔርኒ ይሴብሖ ።
እግዚአብሔርም ያመሰግነዋል
ይገልጸዋል በመስቀል ።
ወሶቤሃ ይሴብሖ ።
ያን ጊዜ ያመሰግነዋል ይገልጸዋል በተእምራት ።
ወዓዲ ካዕበ ይሴብሖ ።
ዳግመኛ ያመሰግነዋል ይገልጸዋል በትንሣኤ የሕፅበተ እግር መገናኛ እንደምን ነው ቢሉ እንደ ሉቃስ ሖሩ ወአስተዳልው ለነ ዘንበልዕ ፍሥሐ ይላቸዋል እንደ ማቴዎስ በአይቴ ትፈቅድ ናስተዳሉ ለከ ፍሥሐ ትብላዕ ይሉታል እንደ ማርቆስ ምልክት ነግሮ ይሰዳቸዋል ሖሩ ሀገረ ዘቅድሜክሙ ወበህየ ትረክቡ ዘይጸውር ፃሕበ ማይ ወትልውዎ ኀበ ቦአ ቤት ወበልዎ ለበዓለ ውእቱ ቤት ይቤለከ ሊቅ ጊዜየ ቀርበ በኀቤከ እገብር ፋሲካ ምስለ አርዳእየ ወውእቱ ያርእየክሙ ጽርሐ ንጡፈ ርሱየ ወስርግወ ወበህየ እስተዳልዉ ለነ ይላቸዋል ወሐዊሮሙ እርዳኢሁ ገብሩ በከመ እዘዞሙ እንዲል በጉን የሚያርዱበት ወቅለምት ደሙን የሚቀበሉበት ብርት ሥጋውን የሚቀቅሉበት ድስት አዘጋጅተዋል ። ወምሴተ ከዊኖ እንደ ማቴዎስ ። ወሶበ ኮነ ጊዜሁ ለድራር እንደ ሉቃስ ። ወእንዘ ይዴረሩ እንደ ዮሐንስ ሲገቡ እንደ ሦስቱ አማን አማን እብለክሙ ከመ ፩ዱ እምኔክሙ ያገብአኒ ይላቸዋል ። እንደ ሁለቱ ወአኃዙ ይተክዙ አርድዕት ወይቤሉ በበ፩ዱ እነኑ እንጋ እግዚእ ይሉታል ፤ ይሁዳም ተለይቼ ብቀር ያውቅብኛል ብሎ እነኑ እንጋ ረቢ አለው ። ለሊከ ትቤ አለው እንድም እንደ ዮሐንስ ወሀሎ ፩ዱ እምአርዳኢሁ ዘይረፍቅ ውስተ ሕፅኑ ለእግዚዚእ ኢየሱስ ወያፈቅሮ እግዚእ ኢየሱስ ወቀጸቦ ስምዖን ጴጥሮስ ሎቱ ተሰአል እንበይኑ መኑ ይብል ዘንተ ወረፈቀ ውእቱ ረድዕ ዲበ እንግድአሁ ወይቤሎ መኑ ውእቱ ያገብእከ ይለዋል ። እንደ ማቴዎስ ዘያወርድ እዴሁ ውስተ መጽብሕየ ። እንደ ሉቃስ እዴሁ ምስሌየ እንደ ዮሐንስ ዘአነ እጸብሕ ሎቱ ኅብስተ ወእሜጥዎ እንደ ዮሐንስ ምልክት ነግሮ እንኾራ በወጥ ጠልቆ ለይሁዳ ሰጠው ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ይሁዳ እንደሆነ ዐውቀው ተጠቃቀሱ ። ወተዋከሁ አርድዕት ይላል ፣ እንደ ሉቃስ ፲ሩ እኛን እኑረውን ሹመት ይካሰሱብናልን ብለዋቸዋል ። ጌታ ኢተእምሩኑ ከመ ነገሥቶሙ ለአሕዛብ ይኴንንዎሙ ወዓበይቶሙ ይቀንይዎሙ ወለክሙሰ አኮ ከማሁ አላ ዘይፈቅድ እምኔክሙ ይኩን ሊቀ ይኩንክሙ ገብረ ይላቸዋል ።

፴፫ ደቂቅየ ኅዳጠ መዋዕለ ሀሎኩ ምስሌክሙ ።
፴፫ ልጆቼ ጥቂት ወራት ከናንተ ጋራ እኖራለሁ ።
ተኃሥሡኒ ። ትሹኛላችሁ ።
ወበከመ እቤሎሙ ለአይሁድ ኀበ አነ አሐውር እንትሙ ኢትክሉ መጺአ ።
ለአይሁድ እናንተ ወደኔ መምጣት አይቻላችሁም ብዬ እንደ ነገርኳቸው ።
ወለክሙኒ ይእዜ እነግረክሙ ።
ለናንተም ዛሬ እነግራችኋለሁ ።

፴፬ ወእሁበክሙ ሐዳሰ ትእዛዘ ።
፴፬ እንግዳ ሥርዓትን እሰጣችኋለሁ ።
ከመ ትትፋቀሩ በበይናቲክሙ
ትፋቀሩ ዘንድ ማለት አንዱ ላንዱ ይሞትለት ዘንድ ።
በከመ አነ አፍቀርኩክሙ ከማሁ አንትሙኒ ተፋቀሩ በበይናቲክሙ ።
እኔ እንደ ወደድኳችሁ እናንተም ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እንደ ሞትኩላችሁ እናንተም አንዱ ላንዱ ይሙትለት ።

፴፭ ወበዝንቱ የአምረክሙ ኵሉ ከመ አማን አርዳእየ አንትሙ ፤

፴፭ አንዱ ላንዱ የሞተለት እንደሆነ በዚህ በውነት የኔ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆናችሁ ሁሉ ያውቃችኋል ።
እምከመ ተፋቀርክሙ በበይናቲክሙ ።
እርስ በርሳችሁ የተዋደዳችሁ እንደሆነ አንዱ ላንዱ የሞተ እንደሆነ ።

፴፮ ወይቤሎ ስምዖን ጴጥሮስ እግዚእ አይቴኑ ተሐውር ።

፴፮ ስምዖን ጴጥሮስም አቤቱ ወዴት ትሄዳለህ አለው ።
ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ኀበስ አነ አሐውር ኢትክል ተሊወትየ ይእዜ ።
እኔን መከተል እኔ ወደምሄድበት ዛሬ መሄድ አይቻልህም ።
ወባሕቱ ድኅረሰ ትተልወኒ ።
ኋላ ግን ትከተለኛለህ ።

፴፯ ወይቤሎ ጴጥሮስ እግዚእ በእንተ ምንት ኢይክል ተሊዎተከ ይእዜ ።

፴፯ ጴጥሮስም አቤቱ ዛሬ አንተን መከተል የማይቻለኝ ስለምን ነው ።
ወእነ ነፍስየ እሜጡ በእንቲአከ ።
እኔ ስላንተ ሰውነቴን ስንኳ አሳልፌ እሰጣለሁ አለው ።

፴፰ ወአ ውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ማቴ. ፳፮ ፴፭ ማር፡፲፬ ፡ ፴ ሉቃ፡፳፪ ፡ ፴፫ ።

፴፰ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ ነፍሰከኑ ትሜጡ በእንቲአየ ኦ ስምዖን ።
ስምዖን ሆይ ስለኔ ብለህ ሰውነትክን ለሕማም ለሞት አሳልፈህ ትሰጣለህን ።
አማን አማን እብለከ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ሥልሰ ትክሕደኒ ።
ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ብዬ እንድ ትክደኝ በውነት እነግርሃለሁ አለው ።
የክሕደተ ጴጥሮስ
መገናኛ እንደምን ነው ቢሉ ፡ ደቂቅየ ዓዲ ኅዳጠ መዋዕለ ሀሎኩ ምስሌክሙ በእንተ ምንት ኢይክል ተልወተከ ይእዜ እስኪል አንብ ። እንደ ማቴዎስ ፡ አማን አማን እብለክሙ ኵልክሙ ትክሕዱኒ በዛቲ ሌሊት እስመ ይብል መጽሐፍ እቀትሎ ለኖላዊ ወይዘረዉ አባግዓ መርዔቱ እንደ ሉቃስ ስምዖን ናሁ ሰአለ ስኢለ ሰይጣን የሐንጽጽክሙ ወየሐን ፍጽክሙ ክመ አለስ ። አንተሰ ተመይጠከ ጸንዖሙ ለአኃዊከ ይለዋል ። እንደ ማቴዎስ እመኒ ኵሎሙ ክሕዱከ አንሰ ኢይክሕደከ ። እንደ ሉቃስ አንሰ ጥቡዕ ለሐዊር ምስሌከ ውስተ ኢየሩሳሌም እመኒ ለመዊት ወእመኒ ለተሞቅሖ ። እንደ ዮሐንስ ነፍስየ ጥቀ እሜጡ በእንቲአከ ይለዋል ። ጌታም እንደ ዮሐንስ ነፍስከኑ ትሜጡ በእንቲአየ ኦ ስምዖን ብሎ እንደ አራቱ አማን አማን እብለከ ዘእንበለ ይንቁ ደርሆ ሥልሰ ትክሕደኒ ይለዋል ። እንደ ማቴዎስ እመውትሂ ምስሌከ ወኢይክሕደከ ይለዋል ፡ ወከማሁ ይቤሎ ኵሎሙ ንመውትሂ ምስሌከ ወኢንክሕደከ ይሉታል እንደ ማርቆስ ወአፈድፈደ ጴጥሮስ ትሕልፍተ ወትምክሕተ እንዘ ይብል እመውትሂ ምስሌከ ወኢይክሕደክ ተመክቶ ያስመካቸዋል ። ወከማሁ ይቤሉ ኵሎሙ ንመውትሂ ምስሌከ ወኢንክሕደከ ይሉታል ።

በእንተ ፍሬያት ዘድኅነት ።

ምዕራፍ ፲፬ ።

፩ ኢይደንግፅክሙ ልብክሙ ።
፩ ሹመት ሽልማት ቀረብን ብላችሁ ልቡናችሁ አይሸበርባችሁ ።
እመኑ በእግዚአብሔር ወእመኑ ብየ ።
ባባቴም በእኔም እመኑ እንጂ ።

፪ እስመ ውስተ ቤተ አቡየ ብዙኅ ማኅደር ወምዕራፍ ቦቱ ።

፪ ባባቴ ቤት በመንግሥተ ሰማይ ብዙ ማዕርገ ሀብታት አለና ። እንድም ኢይደንግፅክሙ እያልክ መልስ ። ፍቅር ክታዘዝ እኛ ካላደረግነው ብላችሁ ልቡናችሁ አይሸበርባችሁ ። እመኑ በእግዚአብሔር ባባቴም በኔም እመኑ እንጂ ። እስመ ውስተ ቤተ አቡየ ባባቴ ቤት በዚህ ዓለም ብዙ ትሩፋት ሥጋ ትሩፋተ ነፍስ አለና ። እንድም ኢይደንግፅክሙ ። መስቀል ክታዘዝ እኛ ካላደረግነው ብላችሁ ልቡናችሁ ኢይሸበርባችሁ ባባቴም በኔም እመኑ እንጂ ። ባባቴ ቤት በወንጌል ብዙ ተዋልጦተ ገድል አለና ። ወናሁ ነገርኩክሙ ክመ አሐወር ወአስተዳሉ ለክሙ መካነ ።
እንድሄድ ልጅነትንም እንዳዘጋጅላችሁ ነገርኳችሁ ።
ወእመ አኮስ እምኢይቤለክሙ ክመ አሐውር ወእስተዳሉ ለክሙ ማኅደረ ።
ያለዚያ ግን ባልነገርኳችሁም ነበር ።

፫ ወእምከመ ሖርኩ ወአስተዳሎኩ ለክሙ መካነ ።
ከሄድኩ ልጅነትንም ፡
፫ ወማኅደረ
መንግሥተ ሰማያትን ።
ወምዕራፈ መስቀልን ፡
ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ ።
እመጽእ ካዕበ ወእነሥአክሙ ኀቤየ ።
ሁለተኛ መጥቼ እኔ ወዳለሁበት እወስዳችኋለሁ ፡
እመጽእ በረድኤት እነሥአክሙ በሞት ።
በረድኤት መምጣቱን በኩት ለመምጣቱ ካዕበ አለው ።
ክመ ተሀልዉ አንትሙኒ ኀበ ሀሎኩ አነ ።
እናንተም እኔ ከምኖርበት ትኖሩ ዘንድ ።

፬ ወለሊክሙ ተአምሩ ኀበ አሐውር ።
፬ እኔ የምሄድበትን አገር ታውቁታላችሁ ።
ወተአምሩ ፍኖቶ ።
መንገዱንም ታውቁታላችሁ ።

፭ ወይቤሎ ቶማስ እግዚኦ ዘኢንአምር ኀበ ተሐውር በአፎ እንክ ነአምር ፍኖቶ ።

፭ ቶማስ እንዲህ አለው አቤቱ የምትሄድበትን አገር የማናውቅ መንገዱን እንደምን እናውቃለን አለው ። አገሩ የታወቀ እንደሆነ የገሌ አገር መንገድ በየት በኩል ነው ተብሎ ተጠይቆ ይኬዳል ።

፮ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አነ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት ።
፮ የሕይወትና የጽድቅ መንገድ እኔ ነኝ ማለት ያንድነት የሦስትነት ባለቤት እኔ ነኝ ።
ወአልቦ ዘይመጽእ ኀበ አብ ዘእንበለ እንተ ኀቤየ

ያለኔ ወደ አብ የሚመጣ የለም እኔን ተወላዲ ካላለ አብን ወላዲ የሚለው የለም ።

፯ አምከመ ኪያየ አእመርክሙኒ እምአእመርክምዎ ለአቡየኒ ።

፯ እኔን ዐውቃችሁኝስ ቢሆን አባቴን ባወቃችሁት ነበር እኔን ተወላዲ ብላችሁኝ ቢሆንስ አባቴንም ወላዲ ባላችሁት ነበር፣እኔ ውእቱ እያልክ መልስ የትሩፋተ ሥጋ የትሩፋተ ነፍስ ጀማሪ እኔ ነኝ ፣ ወአልቦ ዘይመጽእ ኀበ አብ ፡ እኔን አብነት ካላደረገ አባቴን ሥራ አሠራኝ የሚለው የለም ፣ ሶበሰ እኔንስ አብነት አድርጋችሁኝ ቢሆን አባቴንም ሥራ አሠራን ባላችሁት ነበር እንድም የክብረ ሥጋ የክብረ ነፍስ ጀማሪ እኔ ነኝ ። እኔን በዠርካላደረገ አባቴን አከብረኝ የሚለው የለም ። ሶበሰ እኔን በዠር አድርጋችሁኝስ ቢሆን አባቴንም አክብረን ባላችሁት ነበር ወይእዜሰ አእመርክምዎሂ ወርኢክምዎሂ ። ዛሬ ግን አውቃችሁታል አይታችሁታል ።

፰ ወይቤሎ ፊልጶስ እግዚኦ አርእየነሁ ለአብ ወየአክለነ ።

፰ ፊልጶስ አብን አሳየን መስማቱ ይበቃናል። እንድም መስማት በማየት ይፈጸምልናል እንድም ለናፍቆት ለእሜት በደጅ ጽናት ይሆንልናል አለው ።

፱ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ መጠነዝ መዋዕል ሀሎኩ ምስሌክሙ ።

፱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን ያህል ዘመን ከናንተ ጋራ ስኖር ።
ወኢያእመርከኒኑ ፊልጶስ ።
ፊልጶስ አላወቅኸኝምን አለው
ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአብ ።
እኔን ያየ አብን አየ ።
ርእየሰ ዘመለኮት አኮ በሥጋ እላ በኃይል ወበሲብሐት ዘድልው ለመለኮት እንዲል
እፎ አንከ ትብል አርእየነሁ ለአብ ።
እንዴትም ትላለህ አብን አሳየን ።

፲ ኢተአምንሁ ከመ አነ በአብ ወአብ ብየ
፲ እኔ ባባቴ አባቴ በኔ ህልው እንደሆነ አታውቅምን ።
ወዝኒ ቃል ዘነገርኩክሙ አኮ ዘእምኀበ ባሕቲትየ ዘነበብኩ ይህም የነገርኳችሁ ነገር ከራሴ ብቻ አንቅቼ አይደለም ።
አላ አብ ዘሀሎ ብየ ውእቱ ይገብሮ ለዝንቱ ግብር ።
በኔ ህልውና ያለ አብ ይሠራዋል እንጂ ።

፲፩ እመኑ ከመ አነ በአብ ወአብ ብየ ።
፲፩ እኔ በአብ፣ አብ በኔ ህልው እንደሆነ እመኑ ።

ወእመ አኮሰ በእንተ ግብርየ እመኑኒ ።
ያም ባይሆን ሥራዬን አይታችሁ እመኑ ። ይህን ሥራ አምላክ በሠራው እንጂ ዕሩቅ ብእሲ አይሠራውም ብላችሁ ።

፲፪ አማን አማን እብለክሙ ዘየአምን ብየ ግብረ ዘአነ እገብር ውእቱኒ ይገብር ።
፲፪ በኔ ያመነ እኔ የምሠራውን ሥራ እርሱም

ይሠራል ።
ወዘየዓቢ እምኔሁ ይገብር ፡ ከርሱም የበለጠ ይሠራል ብዬ እንዲሠራ በውነት እነግራችኋለሁ ።
እርሱ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ነው ተአምራት ያደረገ እነሱ ብዙ ዘመን ቢኖሩ ብዙ ተአምራት ያደርጋሉና ።
እንድም እርሱ ያሥነሣ ያ፬ ቀን ሬሳ ነው ፡ እነያ የሰባ የሰማንያ ዘመን ሙታን ያሥነሣሉና ይህስ እንዳይሆን እርሱንም እለ አብርሃምን አሥነሣ ይለዋል በተአምረ ኢየሱስ ብሎ የርሱ አይደነቅም ሕያወ ባሕርይ ነው ፡ እነያ ድውይ ሲሆኑ ድውይ መፈወስ ሙት ሲሆኑ ሙትማሥነሣት ይደነቃሉና ። እንድም ወአርባዕቱ እደዊሁ ለሰብእ እንዲል ሞትን ኃጢአትን ፍዳን ሰይጣንን ድል ነሥቷልና ። እንድም ሙት ከማሥነሣት የሚበልጥ ፍቅርን ገንዘብ ያደርጋል ። ዘሰ የዓቅባ ለፍቅር ውእቱ የአቢ እምአለ ያነሥኡ ሙታነ እንዲል ። በእንተ አለ መጽኡ ይትፌጥሩ የሚደረግ ተአምራት አለና ። እስመ ገቢረ ተአምራት ወመንክራት ኢይከል ያድኅን እምዠነኔ ገሃነም እንዷል ። እንድም ከራሱ የበለጠ ተራራን ያፈልሳል ።
እስመ አነ አሐውር ኀበ አብ ፡
እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና ።

፲፫ ወዘሰ ዘሰአልክሙ በስምየ ይገብር ፡ ለክሙ ። ማቴ፣ ፯፥፯ ማር. ፲፩፥፳፬ ዮሐ. ፲፮፥፳፫ ።

፲፫ በቅንው ወልድክ በስቁል ወልዮክ ብላችሁ የለመናችሁትን ያደርግላችኋል ።
ከመ ይስባሕ አብ በወልድ ።
አብ በወልድ ይገልጽ ዘንድ

፲፬ ወእመቦ ዘሰአልክሙ በስምየ እገብር ለክሙ ኪያሁ ።

፲፬ ብትለምኑኝም አብ ያደረገውን አደርግላችኋለሁ ።

፲፭ ወእመሰ ታፈቅሩኒ ዕቀቡ ትእዛዝየ ።
፲፭ ከወደዳችሁኝስ ትእዛዜን ጠብቁ ።

፲፮ ወአነ እሰእሎ ለአብ ይፈኑ ለክሙ ጳራቅሊጦስሃ ካልዓ ዘይሄሉ ምስሌክሙ እስከ ለዓለም

፲፮ ሰዘላለም ከናንተ ጋራ የሚኖር ጰራቅሊጦስን ይልክላችኋል ጰራቅሊጦስ ማለት መጽንኢ መንጽሒ ናዛዚ ከሣቲ መሥተፍሥሒ መስተስርዪ ማለት ነው ።
ከልዓ ባለው አንድ ገጽ የሚል ሰባልዮስ ይረታል ዘከማየ የሚል አብነት ይገኛል መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ የሚል መቅዶንዮስ ይረታበታል ።

፲፯ መንፈስ ጽድቅ ።
፲፯ አካላዊ ባሕርያዊ ሕይወት አከባሪ ሕይወት አንድም መንፈስ ሐሰት አለና ከዚያ ሲለይ መንፈስ ጽድቅ አለ ።
ዘኢይከል ዓለም ነሚአቶ ።
ዓለም እኔን ለሕማም ለሞት አሳልፎ እንዲሰጠኝ ለሕማም ለሞት አሳልፎ ሊሰጠው የማይቻለው አንድም እንደ ግሡሥ ከብት ገንዘብ ሊያደርገው የማይቻለው ።
እስመ ኢይሬእዮ ወኢየአምሮ እያየውም አያውቀውምና ፣ አንድም ዘኢይከል ብለህ መልስ ፈትለ ሣሬት ለንፍሃተ ነፋስ መቆም መቆየት እንዳይቻለው ዓለማዊ ሰውነት ማደሪያው ሊሆን የማይቻለው ። እስመ ኢይሬእዮ ፣ አያየውምና አይወደውምና ።
ወአንትሙሰ ተአምርዎ ።
እናንተ ግን ታውቁታላችሁ ፣
እስመ ውእቱ ኀቤክሙ ይነብር
አድሮባችሁ ይኖራልና ።
ወውስቴትክሙ ይሄሉ ፣
በነፍስ በሥጋ ለማስት ደገመው ፡ በውስጣችሁ ይኖራል ።

፲፰ ወኢየኅድገክሙ ዕጓለ ማውታ ትኩኑ ።
፲፰ ድኆች ትሆኑ ዘንድ አልተዋችሁም ።

፲፱ እስመ አነ እመጽእ ኀቤክሙ ዓዲ
እምድኅረ ኀዳጥ መዋዕል ።

፲፱ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደናንተ እመጣለሁና
ወኢይሬእየኒ እንከ ዓለም ።
ሌላው ሰው አያየኝም ፣
ወአንትሙሰ ትሬእዩኒ
እናንተ ግን ታዩኛላችሁ ።
እስመ አነ ሕያው ።
እኔ ሕያው ነኝና ። በትንሣኤ ።
ወአንትሙኒ ተሐይው ፣
እናንተም ሕያዋን ናችሁና ።

፳ ይእተ አሚረ ተአምሩ ከመ አነ በአብ
ወአብ ብየ ።

፳ እኔ ባባቴ ፣ አባቴ በኔ ህልዋን እንደሆን ያን ጊዜ ታውቃላችሁ ።
ወአንትሙኒ ብየ ።
እናንተም በኔ ታምናላችሁ ።
ወአነኒ ብክሙ ፣
እኔም በናንተ አድርባችኋለሁ

፳፩ ዘቦቱ ትእዛዝየ ወየዓቅቦ ውእቱ ያፈቅረኒ ።

፳፩ በሕጌ የጸና ሕጌን የጠበቀ የሚወደኝ እርሱ ነው ።
ወለዘያፈቅረኒ ያፈቅሮ አቡየ
የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል ያድርበታል ።
ወአነኒ አፈቅሮ ።
እኔም እወደዋለሁ አድርበታለሁ ።
ወአርእዮ ርእስየ ።
ራሴንም እገልጽለታለሁ ።

፳፪ ወይቤሎ ይሁዳ ወአኮ አስቆሮታዊ
፳፪ የአስቆሮት ሰው ያይደለ ይሁዳ ታዴዎስ አለ ።

እግዚኦ ምንትኑ ዘትቤ ከመ ለነ ሀለወከ ታርኢ ርእሰከ ወአኮ ለዓለም ፣
አቤቱ ለዓለም ያይደለ ለኛ ራስህን ትገልጽ ዘንድ እንዳለህ የምትናገረው ምንድነው አለ ።

፳፫ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ
፳፫ ጌታም መለሰለት ።
ወይቤሎ ዘያፈቅረኒ ይዕቀብ ቃልየ ።
የሚወደኝ ሕጌን ይጠብቅ ።
ወያፈቅሮ አቡየ ።
አባቴ ይወደዋል ያድርበታል
ወእመቦ ዘዓቀበ ቃልየ አነ ወአቡየ ንመጽእ ኀቤሁ
ወንገብር ምዕራፈ ውስቴቱ ፣
ሕጌን የጠበቀ ቢኖር ወደርሱ እንመጣለን በርሱም ዘንድ ማደሪያ እናደርጋለን ማለት ሥራ እናሠራዋለን ።

፳፬ ወዘሰ ኢያፈቅረኒ ኢየዓቅብ ቃልየ ።
፳፬ የማይወደኝ ግን ሕጌን አይጠብቅም ።
ወዝኒ ቃል ዘትሰምዑ ኢኮነ ቃለ ዚአየ ።
ይህም የምነግራችሁ ነገር የኔ ብቻ አይደለም ።
አላ ቃሉ ውእቱ ለአብ ለዘፈነወኒ ።
የላከኝ ያባቴም ነው እንጂ ።

፳፭ ወዘንተ ነገርኩክሙ እንዘ ሀሎኩ ምስሌክሙ ።

፳፭ ከናንተ ጋራ ሳለሁ ይህን ነገርኋችሁ ።
፳፮ ወባሕቱ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ጽድቅ ዘይፌኑ አብ በስምየ ውእቱ ይሜህረክሙ ኵሎ ።

፳፮ ነገር ግን በስሜ ብታምኑ አብ የሚልክላችሁ ጰራቅሊጦስ ሁሉን ይገልጽላችኋል ።

ወያዜክረክሙ ዘነገርኩክሙ አነ ።
እኔ የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል ።

፳፯ ሰላምየ አኀድግ ለክሙ ።
፳፯ ወንጌልን እሠራላችኋለሁ ።
ወሰላመ አቡየ እሁበክሙ ።
ልጅነትን እሰጣችኋለሁ። እንድም ሰላምየ መሰቀልን እሻችኋለሁ ። ወሰላመ አቡየ ፡ መንግሥተ ሰማይን አወርሳችኋለሁ አኮ በከመ ይሁብ ዓለም ዘእሁበክሙ አነ ። እኔ የምሰጣችሁ ሰው እንደሚሰጠው ያለ አይደለም ። ሰው ቢሰጥ ያንዱን ሳንዱ ኃላፊውን ነው እርሱ ግን የባሕርዩን ነውና ። እንድም ሰው የሚሰጠው ግዙፉን ነው ። እርሱ ግን ረቂቁን ነውና ፡ ሰው ቢሰጥ ላዝማሪ ለዘዋሪ ነው ፡ እርሱ ግን ለዚህ አይሰጥምና ። እንድም ሰው ቢሰጥ ማፍጀት ፡ መሰልቸት መጸጸት መመረር ። መሰቀቅ አለበት ። በሱ ግን ይህ ሁሉ የለበትምና
ኢይደንግፅክሙ ልብክሙ ።
ልቦናችሁ አይደንግፅባችሁ ።
ወኢትፍርሁ ።
አትፍሩ ። ኢትፍርሁ ለማለት ደገመው ።

፳፰ ሰማዕክሙ ዘእቤለክሙ ከመ አነ አሐውር ወእሰውጥ ኀቤክሙ ።

፳፰ እንድሄድ እንደሰማችሁ ። እንድመለስ ሰምታችኋልና ። እንድም እንድሄድ እንደሰማችሁ እንድሄድ ብትሰሙ እንድመለስም ሰማችሁ ።
ሶበሰ ታፈቅሩኒ እምተፈሣሕክሙ በሐዊርትየ ኀበ አብ
ብትወዱኝስ ወደአብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር።
እስመ ውእቱ አብ የዓብየኒ ።
አብ ያከብረኛልና ይበልጠኛልና ። አኮ እንዘ ይንእስ እም አብ በሕላዌሁ ወበዕሪናሁ ይነግር ዘንተ በእንተ ትስብእቱ እንዲል ።

፳፱ ወይእዜኒ ናሁ ነገርኩክሙ ዘእንበለ ይኩን ከመ እመ ኮነ ትእመኑ ።

፳፱ በተደረገ ጊዜ አስቀድሞ ዐውቆ የነገረን የባሕርይ አምላክ ቢሆን እንጂ ነው ብላችሁ ታምኑኝ ዘንድ ሳይደረግ አስቀድሜ ዛሬ ነገርኋችሁ ።

፴ ወኢይትናገር እንከ ብዙኀ ምስሌክሙ ።

፴ ለክሙ ሲል ነው ለናንተ ብዙ ነገር አልነግራችሁም ።
እስመ ይመጽእ መልአኩ ለዝንቱ ዓለም ።
የዚህ ዓለም አበጋዝ ዲያብሎስ ይመጣልና ።
ወኢይረክብ በላዕሌየ ወኢምንተኒ ።
በኔ ምንም ምን አያገኝብኝም የሐልዮ ስንኳን ኃጢአት አያገኝብኝም ። በሐልዮ እንዳልሠራ ለማጠየቅ እንዲህ አለ በነቢብ እንዳልሠራ ለማጠየቅ ነቢይ ኢገብረ ኃጢአተ ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ ብሏል ። በገቢርም እንዳልሠራ ለማጠየቅ መኑ እምኔክሙ ዘይዛለፈኒ በእንተ ኃጢአት ብሏል።

፴፩ ወባሕቱ ከመ ያእምር ዓለም ከመ አነ አፈቅሮ ለአብ ወበከመ ወሀበኒ አብ ትእዛዞ ከማሁ እገብር ። ማብ፲፪፥፳፪ ።

፴፩ ነገር ግን አብን እንድወደው ሰው ሁሉ ያውቅ ዘንድ ተሰቀል ሙት እንዳለኝ እሰቀላለሁ እሞታለሁ ። እንድም እኔን አብ ። ተሰቀል ሙት እንዳለኝ ተሰቀሉ ሙቱ እላለሁ። ተንሥኡ ንሑር እምዝየ ከዚህ ተነሡ እንሂድ ይሁዳ አራት ቤት ጭፍራ ይዞ የሚመጣ ነውና ምክንያት ሁኝ የሰው ከብት አላዘርፍም ሲል እናንተም ምክንያት ሁናችሁ የሰው ገንዘብ አታዘርፉ ለማለት እብነት ለመሆን እንድም ትምህርት ባይከተትለት ከምሥጢር ወደ ምሥጢር እንሂድ ።

በእንተ ሐረገ ወይን ወበእንተ አዕጹቂሁ ።

ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ አነ ውእቱ ሐረገ ወይን ዘጽድቅ ።
፩ እውነተኛ ሐረገ ወይን እኔ ነኝ አብ ጉንደ ወይን ወልድ ጉንደ ወይን መንፈስ ቅዱስ ጉንደ ወይን እንዲል ።
ወአቡየ ተካሊሁ ።
ተካዩ አባቴ ነው ማለት ግንድ አድራጊው ግን አባቴ ነው ። እንድም አነ ውእቱ ሐረገ ወይን እንደ በሥርነቱ በሥር እኔ ነኝ ። በሥር አድራጊው ግን አባቴ ነው ። ወይን በተተከለ በሦስት ዓመት ዳስ ሠርተውለት ያፈራል ጌታም ማስተማር በጀመረ በሦስት ዓመት ተሰቅሎ ለምእመናን ፍሬ ክብርን ያፈራላቸዋልና ። እንድም ወይን ባመት ባመት አንዳንድ ቃዳ እያከለ ይጸዳል እየቀደም የምትሰፋ ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል ባለፈው ሥጋውን በኅብስት እንደሰጠን ለማጠየቅ ራሱን በኅጠተ ሥርናይ መስሎ እንደተናገረ ከዚህም ደሙን በወይን እንደሰጠን ለማጠየቅ ራሱን በሐረገ ወይን መስሎ ተናገረ ።

፪ ወለኵሉ ዐጽቅ ዘኢይፈሪ በላዕሌየ ይገዝምዎ ።

፪ ወደ ወርቅ ሂዶ በላዕሌየ አለ የማያፈራውን ዕንጨት ሁሉ ይቆርጡታል ።
ወያአትትዎ ።
ይጥሉታል ።
ወለኵሉ ዐጽቅ ዘይፈሪ ያስተናጽሕዎ ።
ለሚያፈራው ዕንጨት ያርሙለታል ይኰተኵቱለታል ።
ከመ ብዙኀ ይፍረይ ።
ብዙ ፍሬን ያፈራ ዘንድ ። እንድም ወለኵሉ ዐጽቅ ዘኢይፈሪ ብሰሀ መልስ ። በኔ አምኖ በጎ ሥራ የማይሠራውን ሰው ሁሉ ሥላሴ ነፍሱን ከሥ

ጋው ይለዩታል። ወለኵሉ ዐጽቅ ዘይፈሪ በጐ ሥራ ለሚሠራ ለምእመን ግን መናፍቁን አውግዘው ይለዩበታል ፫፻ ፲፰ መቶ አርዮስን ፡ መቶ አምሳው መቅዶንዮስን ፡ ሁለት መቶ ንስጥሮስን ። እስከ ምጽአት የሚነሡ መምህራን እስከ ምጽአት የሚነሡ መናፍቃንን ። ከመ ብዙኃ ይፍረይ ምእመናን ብዙ ፍሬትሩፋት ያፈሩ ዘንድ። ወለኵሉ ዐጽቅ ያስተናጽሕዎ ይላል አብነት ። በጐ ፍሬ የሚያፈራውን ዕንጨት ሁሉ ይቆርጡታል ። ከመ ብዙኃ ይፍረይ። በጐው ዕንጨት ብዙ ፍሬ ያፈራ ዘንድ። በጐ ሥራ ለሚሠራው መናፍቁን አውግዘው ይሰዱታል ምእመንም ብዙ ፍሬ ትሩፋትን ያፈራ ብዙ ፍሬ ክብርን ያገኝ ዘንድ ።

፫ ወአንትሙሰ ወዳእክሙ ንጹሐን አንትሙ በእንተ ቃል ዘነገርኩክሙ ። ዮሐ. ፲፫ ፲፱ ፡ ፲ ።

፫ እናንተ ግን እኔ ባላስተማርኳችሁ ፊጽማችሁ ንጹሐን ናችሁ ።

፬ ንበሩ ብየ ።

፬ በትምህርቴ ጸንታችሁ በኔ እምናችሁ ኑሩ ።
ወእነሂ ብክሙ ።
እኔም በናንተ አድሬባችሁ እኖራለሁ ።

፭ ወበከመ ዐጽቅ ኢይክል ፈርየ ባሕቲቱ እመ ኢሀሎ ውስተ ጕንደ ወይኑ ።

፭ ክጉንዱ የተለየ ዐጽቅ ማፍራት እንዳይቻለው ።
ከማሁ አንትሙኒ ኢትክሉ ፈርየ ለእመ ኢነበርክሙ ብየ ። እናንተም በኔ ካላመናችሁ ሥራ መሥራት አይቻላችሁም ።
እነ ውእቱ ጕንደ ወይን ዘጽድቅ ።
ጉንደ ወይን እኔ ነኝ ።
ወአንትሙሂ ዐፀዱቂሁ ።
ዐጽቆቹም እናንተ ናችሁ ።
ዘነበረ ብየ በኔ ባመነ
ወአነሂ ቦቱ ።
እኔም አድሬበት እኖራለሁ ፡ ውእቱ ማንኛ አንድም በኔ ያመነ እኔ ያደርኩበት ።
ውእቱኬ ዘይፈሪ ብዙኃ ፡
ብዙ ፍሬ ትሩፋትን የሚያፈራ ብዙ ፍሬ ክብርን የሚያገኝ እርሱ ነው ።
እስመ ዘእንበሌየሰ አልቦ ዘትክሉ ገቢረ ወኢምንተኒ በኔ ካላመናችሁ ምንም ምን ሥራ መሥራት አይቻላችሁምና ።

፮ ወእመቦ ዘኢነበረ ብየ ይገድፍዎ ፍእአ ከመ ዐጽቅ ይቡስ

፮ በኔ ያላመነ ሰው ቢኖር ይቡስ ዐጽቅ እንደ መሆኑ እንደ ይቡስ ዐጽቅ እንደ አቤል ነፍሱን ከሥጋው ይለዩታል ። አንድም ከመ ዐጽቅ ይየብስ ይላል ነፍሱ ከሥጋው ይለያል ፡
ወያወፅእዎ ።
ከቤት ያወጡታል ። ወይገድፍዎ በመቃብር ይጥሉታል ። ወያነሥእዎ ፡ በትንሣኤ ያነሡታል ።
ወያውዕይዎ በእሳት ።
በገሃነም ፍዳ ያመጡበታል ። አንድም ይገልይዎ ወይገምድዎ ያወፅእዎ ወይገድፍዎ ያስተጋብእዎ ወያነሥእዎ ወያውዕይዎ ይላል አብነት ፡ ይገልይዎ ነፍሱን ከሥጋው ፡ ይገምድዎ ሥጋውን ከነፍሱ ይለዩታል ። ያወፅእዎ ከቤት ፡ ይገድፍዎ በመቃብር ያስተጋብእዎ በትንሣኤ ዘጉባኤ ያነሥእዎ ፡ ያሥነሡታል ያውዕይዎ በገሃነም ፍዳ ያመጡብታል ።

፯ ወእመሰ ነበርክሙ ብየ ፡
፯ በኔ አምናችሁ ብትኖሩ ፡
ወነበረ ቃልየ ኀቤክሙ ።
ያስተማርኳችሁም ትምህርት ብናንተ ጸንቶ ቢኖር ።
ኵሉ ዘፈቀድክሙ ይከውን ለክሙ ።
የሻችሁት ሁሉ ይደረግላችኋል ።

፰ ወበዝንቱ ይሴባሕ አቡየ እምከመ ብዙኃ ፍሬ ትፈርዩ ።

፰ ብዙ ፍሬ ትሩፋት እንድታፈሩ ብትሆኑ ።
ወትከውኑኒ አርዳእየ እምጸማክሙ ።
ከጻማ እሬት ተለይታችሁ የኔ ደቀ መዛሙርት እንድትሆኑ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይመሰገናል ። አንድም በዝንቱ ይሰባሕ ይላል ፡ በዚህ አባቴ ይመሰገን ዘንድ ። ከመ ትፍረዩ ፡ ፍሬ ትሩፋትን ታፈሩ ዘንድ ፡ ወትከውኑ ። የኔ ደቀ መዛሙርት ትባሉ ዘንድ ። እምጻማክሙ አምጸእኩክሙ ። ከጻማ እሬት ለይቼ አመጣኋችሁ ።

፱ ወበከመ አፍቀረኒ አብ ከማሁ አነኒ አፍቀርኩክሙ ።

፱ አባቴ እኔን እንደ ወደደኝ አወዳችኋለሁ ትሰቀል ሙት እንዳለኝ ተሰቀሉ ሙቱ እላችኋለሁ።
ሀልዉ በፍቅረ ዚአየ ።
በኔ ፍቅር ጸንታችሁ ኑሩ ።

፲ ወእመሰ ታፈቅሩኒ ዕቀቡ ትእዛዝየ ።
፲ ከወደዳችሁኝ ትእዛዜን ጠብቁ ።
ወሀልዉ በፍቅረ ዚአየ ።
በኔ ፍቅር ጸንታችሁ ኑሩ ።
በከመ ዓቀብኩ አነ ኵሎ ትእዛዞ ለአቡየ ።
እኔ ያባቴን ትእዛዛት እንደ ጠበቅሁ ።
ወእሄሉ በፍቅሩ ።
በፍቅሩም ጸንቼ እንዳለሁ ፡ ዕቀቡ ሀልዉ ብሎ ።

፲፩ ወነገርኩክሙ ዘንተ ።
፲፩ ይህን ነገርኳችሁ ።
ከመ የሀሉ ሐብየ ወፍሥሐየ ወፍቅርየ ኀቤክሙ ።

ልብየ ትምህርት፣ፍሥሐየ ልጅነት ። ፍቅርየ መስቀል በናንተ ዘንድ ጸንቶ ይኖር ዘንድ ፣
ከመ ፍጹመ ይኩን ፍሥሐክሙ ።
ፈጽሞ ደስ ይላችሁ ዘንድ ።

ዘከመ ይደልዎሙ ለአኃው ተፋቅሮ ።

፲፪ ወዛቲ ይእቲ ትእዛዝእንቲአየ ወዘንተ እዘዝኩክሙ ከመ ትትፋቀሩ በበይናቲክሙ በከመ አነ አፍቀርኩክሙ ። ዮሐ፣ ፲፪፡፴፬ ኤፌ፡፭፡፪ ፩ ተሰ፡፬፡፱።

፲፪ እኔ እንደ ወደድኳችሁ እናንተ በናንተ ትዋደዱ ዘንድ ማለት እኔ እንደ ሞትኩላችሁ አንዱ ላንዱ ይሞትለት ዘንድ ይህን ነገርኳችሁ ።

፲፫ አልቦ ዘየዓቢ ወይኄይስ እምዝፍቅር ከመ ብእሲ ዘይሜጡ ነፍሶ ቤዛ ቢጹ ።

፲፫ ሰውነቱን ለባልንጀራው ቤዛ አድርጎ ለሕማም ለሞት አሳልፎ እንዲሰጥ ከመሆን ፣ እንዲሰጥ ሁኖ ከመገኘት እንዲሰጥ ሁኖ ተገኝቶ ከዚህ የበለጠ ፍቅር የለም ። ታሪክ አበምኔቱ ሲቀድስ የሚለብሰው ክቡር ልብስ አለ ከማኅበሩ አንዱን ሰይጣን አገብሮት አንሥቶ ሰውሮታል አምጡ አለ ። ቢፈልጉ አጡት ከዚያው አንድ ደግ ሰው አለ ያ ሰው ከዚያ ሂዶ ይጫወታል ደወል መቱ ደወሉን ሰምቶ ደነገጠ ምነው ደነገጥክ አለው ይህን የሚፈልጉትን ዕቃ ሰይጣን አገብሮኝ ወስጄ ሰውሬ ነበር አለው አምጥተህ አኑረኸው ሂድ አለው አምጥቶ አኑሮት ሄደ መጥተው እጅ ጸፉ ፣ ወጥቶ ምነው አላቸው ፣ ገንዘብ ጠፍቶን እንፈልጋለን አባታችን አንተን ጠርጥረንህ አይደለም ከሰው ተለይተህ እንዳትቀር ብለን ነው እንጂ አሉት ፣ ገብታችሁ ፈልጉት ምን ዐውቃችሁ አላቸው ፣ ቢገቡ አገኙት አልሰወረውምና ፣ ላየ ደህና ውከጠ ቀጣፊ ብለው ገርፈው ወገድ ውጣልን አሉት ሁለት ቅጣት አቀጣለሁን ቀኖናየን ስጡኝና ከዚሁ ላድርስ እንጂ አላቸው አይሆንም ከሌባ ጋራ አንኖርም አሉት ልብሱን አናንሣህ ቢሉት የማይነጣ ሆነ ። ነገሩስ ካልቀረ ብሎ የወሰድኩ እኔ ነኝ አለ። እርሱ በኔ ኃጢአት ነው የተገረፈው ብሎ ገልጦ ተናገረ ጌታ በወንጌል እንዲህ ያለው ይህን ነው ብለው አድንቀዋል ። ።

፲፬ አንትሙሰኬ አእርክትየ አንትሙ እምከመ ገበርክሙ ኵሎ ዘአዘዝኩክሙ ።

፲፬ እናንተም ያዘዝኳችሁን ሁሉ ብታደርጉ ወዳጆቼ ናችሁ ።

፲፭ ኢይብለክሙ እንከ አግብርትየ ።
፲፭ እንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም ።
አላ አእርክትየ አንትሙ ።
ወዳጆቼ እላችኋለሁ እንጂ ።
እስመ ገብርሰ ኢየአምር ዘይሬስዮ እግዚኡ ።
ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቀውም ይሸጠው ይለውጠው ማጫ ትሎት አሳልፎ ይሰጠውም እንደሆነ አያውቀውም ።
ወለክሙሰ አእርክትየ እብለክሙ ።
እናንተንስ ወዳጆቼ እላችኋለሁ ።
እስመ ኵሎ ዘሰማዕኩ በኀበ አቡየ ነገርኩክሙ ።
ከባቴ በህልውና የሰማሁትን ነግሬያችኋለሁና ።

፲፮ አኮ አንትሙ ዘኀረይክሙኒ ወሜምክሙኒ ማቴ፡፳፰ ፡ ፲፱ ።

፲፮ ነገር ግን ማኅበር አባቱን፣ ጭፍራ ፡ አለቃውን መርጦ እንዲሾም እናንተ መርጣችሁ የሾማችሁኝ አይደለም ።
አላ አነ ኃረይኩክሙ ወሜምኩክሙ ።
እኔ መርጬ ሹሜያችኋለሁ እንጂ ።
ወአሬስየክሙ ከመ ትሑሩ ።
እንድትሄዱ ማለት በሃይማኖት ጸንታችሁ እንድትኖሩ ።
ወፍሬ ትፍረዩ ።
ፍሬ ትሩፋትን እንድታፈሩ አደርጋችኋለሁ ።
ወውእቱ ፍሬክሙ ይንብር ለዓለም ።
ፍሬ ትሩፋታችሁም ለዘለዓለም ይኖራል ።
ከመ እመ ሰአልክምዎ ለአብ በስምየ ኵሎ ይሁበክሙ በቅንው ወልድከ በስቁል ወልድከ ብላችሁ ብትለምኑት አብ እንዲያደርግላችሁ መጠን ።

፲፯ ወዘንተ እኤዝዘክሙ ከመ ትትፋቀሩ በበይናቲክሙ ። ፩ ዮሐ፣ ፫፣ ፲፩ ።

፲፯ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አንዱ ላንዱ ይሞትለት ዘንድ ይህን ነገርኳችሁ ።

በእንተ ጸልአ ዝንቱ ዓለም ።

፲፰ እመኒ ዓለም ጸልአክሙ አእምሩ ከመ ኪያየ ተደመ ጸሊአ ።

፲፰ ሰው ቢጠላችሁም አስቀድሞ እኔን እንደጸላኝ ዕወቁ ።

፲፱ ሶበሰ እምዓለም አንትሙ እምአፍቀረክሙ ዓለም ።

፲፱ ከዓለም ወገን ብትሆኑ ሰው በወደዳችሁ ነበር ።
እስመ ዓለም አሊአሁ ያፈቅር ።
ወገን ወገኑን ይወዳልና ሌባ ሌባውን ቀጣፊ ቀጣፊውን ።
ወባሕቱ እስመ ኢኮንክሙ እምዓለም ።
እናንተ ግን ከዓለም ወገን አይደላችሁም ።
አላ አነ ኃረይኩክሙ እምውስተ ዓለም ።

እኔ ከዓለም መርጫችኋለሁ እንጂ ።
በእንተ ዝንቱ ይጸልአክሙ ዓለም ።
ስለዚህ ሰው ይጠላችኋል ።

፳ ተዘከሩ ቃልየ ዘአነ እቤለክሙ አልቦ ገብር ዘየዓቢ እምእግዚኡ ወኢሐዋርያ ማቴ፡፲፡፳፬፡ዮሐ፡፲፫፡፲፮ ። ማቴ፡፳፬፡፱ ።

፳ በዚያውም ላይ ከጌታው የሚበልጥ ባሪያ ከላኪው የሚበልጥ መልክተኛ የለም ያልኳችሁን አስቡ ።
እምከመ ኪያየ ሰደዱ ኪያክሙኒ ይሰድዱክሙ ።
እኔን በሞት አስወጥተው ከሰደዱኝ እናንተንም ከሀገራችሁ አስወጥተው ይሰዱዋችኋል ።
ወሶበሰ ዓቀቡ ቃልየ ቃለክሙኒ እምዓቀቡ ።
ነገሬን ተቀብለውኝስ ቢሆን እናንተንም በተቀበሏችሁ ነበር

፳፩ ወባሕቱ ዘንተ ኲሎ ይገብሩ ላእሌክሙ በእንተስምየ እስመ ኢየአምርዎ ለዘፈነወኒ ።

፳፩ ነገር ግን አባቴን አያውቁትምና በኔ ስም ስለአስተማራችሁ ይህን ሁሉ ያመጡባችኋል።
አንድም በኔ ስም ስለአስተማራችሁ ፤ ይህን ሁሉ የሚያመጡባችሁ አባቴን አያውቁትምና ስለዚህ ነው ።

፳፪ ሶበሰ ኢመጻእኩ አነ ወኢነገርክዎሙ እምድኅኑ ወእምኢኮኖሙ ጌጋየ ።

፳፪ ሰው ሁኜስ ባላስተማርኋቸው ዕዳ ባልሆነባቸው ነበር ከፍዳም በዳኑ ነበር ።
ወይእዜሰ ባሕቱ አልቦሙ ምክንያት ለጌጋዮሙ ።
ዛሬ ግን ለበደላቸው ምክንያት የላቸውም ። ባናውቅ ያስተምረን ባይኖር አይሉም ።

፳፫ ዘጸልዓ ኪያየ ጸልዓ ለአቡየ ።
፳፫ እኔን የጠላ አባቴን ጠላው ።
፳፬ ሶበሰ ኢገበርኩ ሎሙ ግብረ ዘባዕድ ኢገብሮ እምኢኮኖሙ ጌጋየ ።

፳፬ ሌላ ያልሠራው ሥራስ ባልሠራላቸው ዕዳ ባልሆነባቸውም ነባር ፤ ምነው ኤልያስ አንድ ምውት ኤልሣዕ ሁለት ምውት አስነሥተው የለምን ቢሉ የኒያ ሕጸጽ አለበት፤የሱ ግን ሕጸጽ የለበትምና። የኒያ የጸጋ ነው ፤ የርሱ የባሕርይ ነውና ።
ወይእዜሰ ባሕቱ ርእዩኒ ወጸልኡኒ ።
ዛሬ ግን አዩኝ ጠሉኝ ።
ኪያየኒ ወአቡየኒ ።
አንድም እኔንም አባቴንም አዩን ጠሉን ።

፳፭ ወባሕቱ ከመ ይብጻሕ ቃል ዘጽሑፍ ውስተ ኦሪቶሙ ዘይቤ ጸልኡኒ በከንቱ ፤ መዝ፡ ፴፬ ሉቃ. ፳፬ ፣ ፵፬ ።

፳፭ ነገር ግን በኦሪት ጽልዓ በዓመፃ ይጸልዑኒ ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ በከንቱ ጠሉኝ ።

፳፮ ወሶበ መጽአ ጰራቅሊጦስ ዘአነ እፌኑ ለክሙ ዘይወፅእ እምአብ ውእቱ ሰማዕትየ ።

፳፮ ከአብ የሚወጣ እኔ የምልከላችሁ ጰራቅሊጦስ በመጣ ጊዜ ምስክሬ ነው ።

፳፯ ወአንትሙኒ ሰማዕትየ ።
፳፯ እናንተም ምስክሮቼ ናችሁ ።
እስመ እምትካት ሀለውክሙ ምስሌየ ኅሩያንየ ።
ተመርጣችሁ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከኔ ጋራ ነበራችሁና አንድም ዕሩይየ ይላል አብነት ከጥንት ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በዕሪናየ አለና ።

በእንተ ሰደታት ።

ምዕራፍ ፲፮

፩ ወዘንተ ነገርኩክሙ ከመ ኢትትዓቀፉ
፩ እንዳትጠራጠሩ ይህን ነገርኋችሁ ።
፪ እስመ እምኵራባቲሆሙ ያወፅኡክሙ

፪ ከምኵራባቸው ያወጧችኋልና
ወባሕቱ ትመጽእ ሰዓት ወይበጽሕ ጊዜሁ ከመ ኲሉ ዘይቀትለክሙ ይመስሎ ከመ ዘመሥዋዕተ ያበውእ ለእግዚአብሔር ።
ባሕቱ ዋዌ ነው እናንተን የገደለ ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀረበ የሚመስልበት ጊዜ ይደርሳል ።

፫ ወዘንተኒ ዘይገብሩ ላዕሌክሙ
፫ ይህንም የሚያደርጉባችሁ ።
እስመ ኢየአምርዎ ለአብ ።
አብን አያውቁትምና ።
ወኢኪያየ ።
እኔንም አያውቁኝምና አንድም መከራ የሚያመጡባችሁ እኔንም አባቴንም አያውቁንምና ስለዚህ ነው ።

፬ ወባሕቱ ዘንተሰ ነገርኩክሙ ከመ ትዘከርዎ አመ በጽሐ ጊዜሁ

፬ ነገር ግን በተደረገ ጊዜ እኔ እንደነገርኋችሁ ታስቡት ዘንድ ይህን ነገርኋችሁ ሳይደረግ አስቀድሞ ዐውቆ የነገረን የባሕርይ አምላክ እንጂ ቢሆን ነው ብላችሁ ታስቡት ዘንድ ።
፭ ወቀዲሙሰ ኢነገርኩክሙ ዘንተ ።
፭ አስቀድሞ ግን ይህን አልነገርኋችሁም ።
እስመ ሀሎኩ ምስሌክሙ ።
ከናንተ ጋራ በሕይወት ነበርኩና ።
ወይእዜሰ ባሕቱ አሐውር ኀበ አብ ዘፈነወኒ ።
ነገር ግን ወደላከኝ ወደ አብ እሄዳለሁ ።
ወኢ፩ዱሂ እምኔክሙ ኢትብሉኒ አይቴ ተሐውር።

ከናንተ አንዳችሁ ስንኳ ወዴት ትሄዳለህ አትሉኝም አብራችሁኝ አትሞቱም ።

፮ ወባሕቱ እስመ ዘንተ ነገርኩክሙ ኀዘን መልአ ውስተ ል ብክሙ ።

፮ ባሕቱና ባሕቱ አንድ ወገን ይሆንስ ሰለነ ገርኋችሁ በልባችሁ ኀዘን ሰፍሮባችኋል ።

ዘከመ አሰፈዎሙ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ።

፯ ወአንስ አማን ህልወ ኢብለክሙ ።
፯ እኔስ ቀዋሚ ነገር ነገርኋችሁ ።
ይኄይስከሙ ኢሑር አነ ኀበ አብ
ወደ አብ እኔ ብሔድ ይሻላችኋል ።
እስመ እመ ኢሖርኩ አነ ኢይመጽእ ጰራቅሊጦስ ኀቤክሙ
እኔ ካልሄድኩ መንፈስ ቅዱስ አይሰጣችሁምና ።
ወእመሰ ሖርኩ አነ ኀበ አብ እፌንዎ ለክሙ ።
እኔ ወደአብ የሄድኩ እንደሆነ ግን እልክላችኋለሁ።

፰ ወመጺአ ውእቱ ይዛለፎ ለዓለም በእንተ ኃጢአት ።

፰ በመጣም ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሰውን ይዘልፈዋል ።
ወበእንተ ጽድቅ ።
በጽድቅ ምክንያት ።
ወበእንተ ኵነኔ ።
በኵነኔም ምክንያት ይዘልፈዋል ። ሦስት አርእስት ተናገረ ። ስምስቱም ያመጣል ።
በእንተ ኃጢአትስ ።
በኃጢአትም ምክንያት ይዘልፈዋል ያልኋችሁ ።

፱ እስመ ኢየአምኑ ብየ ።
፱ አላመኑብኝምና ስለዚህ ነው ።
አስተኃፈረ ኃጢአተ በዲበ ምድር ብለው ይነግሯቸዋል በዚህ ባያምኑ ድውይ ፈውሰው ያሳዩዋቸዋል በዚያ ባያምኑ ዕዳ ይሆንባቸዋልና ።

፲ ወበእንተ ጽድቅ ።
፲ በጽድቅ ምክንያት ይዘልፈዋል ያልኩት ።
እስመ አነ አሐውር ኀበ አብ ወደአብ እሄዳለሁና ።
ወኢትሬእዩኒ እንከ ።
ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝምና ስለዚህ ነው ። አብ ጠለ ሞተ በውስተ ሲኦል ወነሥተ ሙስና በውስተ መቃብር ብለው ይነግሯቸዋል በዚህ ባያምኑ ሙት አሥንሥተው ያሳዩዋቸዋል በዚህ ባያምኑ ይፈረድባቸዋልና ።

፲፩ ወበእንተስ ኵነኔ እስመ ይትኴነን መል አኩ ለዝንቱ ዓለም ።

፲፩ በኵነኔ ምክንያት ይዘልፈዋል ያልኩት የዚህ ዓለም አበጋዝ ዲያብሎስ ድል ይነሣልና ስለ ዚህ ነው ። ወሠዓረ መርገመ በዲበ ዕፀ መስቀል ብለው ይነግሩዋቸዋል በዚህ ባያምኑ ጋኔን አውጥተው ያሳዩዋቸዋልና በዚያ ባያምኑ ዕዳ ይሆን ባቸዋልና ። አንድም በእንተ ኃጢአት አስተኃፈረ ኃጢአተ በዲበ ምድር ወአብጠለ ሞተ በውስተ ሲኦል ብለው ይነግሩዋቸዋል በዚህ ባያምኑ ድውይ ፈውሰው ሙት አሥነሥተው ያሳዩዋቸዋል በዚህ ባያምኑ ይፈረድባቸዋል ። ወበእንተ ጽድቅስ እም ቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ ብሏል ብለው ይነግሩዋቸዋል በዚህ ባያምኑ ከራሳቸው አንቅተው ቀዳሚሁ ቃል ብለው ይነግሩዋቸዋል፤ በዚህ ባያምኑ ዕዳ ይሆንባቸዋልና ። ወበእንተ ኵነኔ አይለወጥም ።

፲፪ ወብየ ብዙኃ ነገረ ዘእነግረክሙ ።
፲፪ የምነግራችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ ።
ወባሕቱ ኢትክሉ ጸዊሮቶ ይእዜ ።
ለብዎቶ ሲል ነው ። ነገር ግን ዛሬ ማወቅ አይቻላችሁም ።

፲፫ ወመጺአ ውእቱ መንፈስ ጽድቅ ይመር ህክሙ ኀበ ኵሉ ጽድቅ ።

፲፫ መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ወደትሩፋተ ሥጋ ወደትሩፋተ ነፍስ መርቶ ያደርሳችኋል ።
እስመ ኢይነግር ዘእምኅቤሁ ፤
ከራሱ አንቅቶ አያስተምርምና ፤
ወዘሰምዐ ዳዕሙ ይነግር ።
ከኔ በህልው የሰማውን ያስተምራል እንጂ።አንድም ከርሱ ብቻ አንቅቶ አይናገርም ከአብ ከኔም በህ ልውና የሰማውንም ያስተምራል እንጂ ።
ወዘይመጽእኒ ይነግረክሙ ፤
ዘይመጽእ ጰራቅሊጦስ ይነግራችኋል ። አንድም ያለፈውን ብቻ አይነግራችሁም የሚመጣውንም ይነ ግራችኋል ።

፲፬ ወውእቱ ኪያየ ይሴብሕ ።
፲፬ እርሱ እኔን ይገልጻል ።
እስመ እምዚአየ ይነሥእ ወይነግረክሙ ።
እግዝእናትን መምህርነትን ቃልነትን ትንቢትን ዘመ ንን ከኔ ገንዘብ ያደርጋልና ይነግራችኋል ።
እስመ ኵሉ ዘቦ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ ፤
ያባቴ ገንዘብ ሁሉ ገንዘቤ ነውና ።

፲፭ ወበእንተ ዝንቱ እብለክሙ እምዚአየ ይነ ሥእ ወይነግረክሙ ኵሎ ።

፲፭ ስለዚህ ከኔ ገንዘብ አድርጎ ሁሉን ይነ ግራችኋል እላችኋለሁ ።

በእንተ ተመይጦተ ኢየሱስ ውስተ ሰማይ ።

፲፮ ዓዲ ኅዳጠ ኢትሬእዩኒ ።
፲፮ ጥቂት ወራት አታዩኝም ።
ወካዕበ ኅዳጠ ትሬእዩኒ ።
ዳግመኛ ጥቂት ወራት ታዩኛላችሁ ።
እስመ አሐውር ኀበ አብ ።
ወደአብ እሄዳለሁና ።

፲፯ ወተበሀሉ አርዳኢሁ በበይናቲሆሙ ምንትኑ ዝንቱ ዘይብለነ ዓዲ ኅዳጠ ኢትሬእዩኒ ወካዕበ ዓዲ ኅዳጠ ትሬእዩኒ ።

፲፯ ደቀ መዛሙርቱ እርስ በርሳቸው ጥቂት ወራት አታዩኝም ጥቂት ወራት ታዩኛላችሁ የሚለን ምንድነው ።
እስመ አሐውር ኀበ አብ ።
ወደአብ እሄዳለሁና ።

፲፰ ወይቤሉ ምንትኑ ዝንቱ ዘይብለነ ኅዳጠ።
፲፰ ጥቂት ወራት አታዩኝም የሚለን ምንድነው
ኢነአምር ዘይትናገር ቦቱ ።
የሚናገረውን አናውቀውም አሉ ።

፲፱ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ይፈቅዱ ይሰአልዎ

፲፱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሊጠይቁት እንደወደዱ አውቆ ወይቤሎሙ በእንተ ዝንቱ ትትኃሠሡ በበይናቲክሙ እስመ እቤለክሙ ዓዲ ኅዳጠ ኢትሬእዩኒ ወካዕበ ኅዳጠ ትሬእዩኒ ጥቂት ወራት አታዩኝም ጥቂት ወራት ታዩኛለችሁ ብያችኋለሁና ስለዚህ እርስ በርሳችሁ ትመራመራላችሁን አላቸው።

፳ አማን አማን እብለክሙ ከመ ትበክዩ ወትላህዉ አንትሙ ።

፳ እንድታለቅሱ እንድታዝኑ በውነት እነግራችኋለሁ አላቸው ።
ወዓለምሰ ይትፌሣሕ ።
ዓለም ግን ደስ ይለዋል ፡
ወአንትሙሰ ትኀዝኑ ፡
እናንተም ታዝናላችሁ ።
ወባሕቱ ኃዘንክሙ ፍሥሐ ይከውንክሙ ።
ነገር ግን ኃዘናችሁ ደስ ያሰኛችኋል ።

፳፩ በከመ ብእሲት ትቴክዝ ሶበ አልጸቀት ለወሊድ ።

፳፩ ለመውለድ የቀረበች ሴት እንድታዝን።
እስመ በጽሐ ጊዜሃ ።
የምትወልድበት ጊዜ ደርሷልና ።
ወእምከመ ወለደት ዕጓላ ኢትዜክሮ እንከ ለሕማማ በእንተ ፍሥሐሃ።
ልጇዋን ከወለደች በኋላም ደስ ስላላት መከራዋን እንዳታስበው ።
እስመ ወለደት ብእሴ ውስተ ዓለም ።
በዚህ ዓለም ወንድ ልጅ ወልዳለችና ።

፳፪ ወከማሁ አንትሙኒ ትቴክዙ ይእዜ ።
፳፪ እርሷ እንዳዘነች እናንተም ታዝናላችሁ።
ወባሕቱ ካዕበ እሬእየክሙ ወይትፌሣሐክሙ ልብክሙ ።
ነገር ግን እርሷን ደስ እንዳላት እናንተም ደስ ይላችኋል አንድም በከመ ብእሲት ብለህ መልስ። ልወለድላቸው የቀረብኩ ነቢያት አምስት ሺህ፡ ካምስት መቶ ዘመን ያዝኑ እንደነበረ ። እስመ በጽሐ ጊዜሃ እኔ የምወለድበት ዘመን ቀርቧልና። ወእመከመ ወለደት ። እኔ ከተወለኩላቸው በኋላ ግን አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን የነበረውን መከራ እንዳያስቡት ። በእንተ ፍሥሐሃ ደስ ስላላቸው ። እስመ ወለደት እኔ ተወልጄላቸዋለሁና። ከማሁ አንትሙኒ። እኒያ ያዝኑ እንደነበረ እናንተም ታዝናላችሁ ወባሕቱ ። እኒያን ደስ እንዳላቸው እናንተንም ደስ ይላችኋል ወፍሥሐክሙኒ አልቦ ዘየሐይደክሙ ።
ከደስታችሁ ከኔ አንድነት የሚለያችሁ የለም ።

፳፫ ወይእተ አሚረ አልቦ ዘትስእሉኒ ኪያየ ወኢምንተኒ ። ማቴ፡፯፡፯ ማር፡፲፩፡፳፬ ሉቃ፡ ፲፩፡፱ ዮሐ፡፲፬፡፲፬ ያዕ፡ ፩፡፭ ።

፳፫ ያን ጊዜ እኔን የምትለምኑኝ ምንም ምን የለም ።
አማን አማን እብለክሙ ከመ እመ ሰአልክምዎ ለአብ በስምየ ኵሎ ይሁበክሙ ።
በቅንው ወልድከ በስቁል ወልድከ እያላችሁ አብን ብትለምኑት የለመናችሁትን ሁሉ እንዲያደርግላችሁ በውነት እነግራችኋለሁ ።

፳፬ ወእስከ ይእዜ ኢሰአልክምዎ ወኢምንተኒ በስምየ ።
፳፬ ነገር ግን እስካሁን ምንም ምን በስሜ አላመናችሁትም ።
ሰአሉ ወትነሥኡ ።
ለምኑ ታገኛላችሁ ።
ከመ ፍጹመ ይኩን ፍሥሐክሙ ።
ፈጽሞ ደስ ይላችሁ ዘንድ ።

ዘከመ ተሰናአለ ኢያሱስ እም አርድዕት ።

፳፭ ወይእዜሰ በምሳሌ ነገርኩክሙ
፳፭ የአብን ነገር ገልጬ ነገርኳችሁ።
ወባሕቱ ይበጽሕ ጊዜሁ አመ ኢይነግረክሙ በምሳሌ።

ነገር ግን ገልጬ የማልነግራችሁ ጊዜ ደርሷል ፡
አላ ክሡተ እየድዓክሙ በእንተ አብ ።
የአብን ነገር በልቦናችሁ እስልባችኋለሁ እቀርጽ
ባችኋለሁ እንጂ ። እንዲህስ እንዳይሆን ።
ወይእዜሰ ገሃደ ተናገርከነ ወአልቦ ዘመሰልከ ብሎ
ያመጣዋል ወይእዜሰ በምሳሌ ነገርኩክሙ ብለህ
መልስ ዛሬ የአብን ነገር ሰውሬ ነገርኳችሁ ። ወባ
ሕቱ ግንሰውሬ የማልነግራችሁ ጊዜ ደርሷል ፡ አላ እየ
ድዓክሙ ክሡተ ፡ ገልጬ እነግራችኋለሁ እንጂ ።

፳፮ ወይእተ አሚረ ትስእሉ በስምየ ።
፳፮ ያን ጊዜ በቅንው ወልድከ በዕቁል ወል
ድከ ብላችሁ ትለምናላችሁ ።
ወኢይብለክሙ ከመ አነ ዘእስእሎ ለአብ በእንቲ
አክሙ ።
ለናንተ አብን እንዳለምነው አልነግራችሁም ።

፳፯ ወአኮ ዘእስእሎ ለአብ በእንቲአክሙ ።
፳፯ ስለናንተ አብን አለምነውም ።
እስመ ለሊሁ አብ ያፈቅረክሙ ።
እርሱ አብ ይወዳችኋልና ።
እስመ አንትሙ አፍቀርከሙኒ ወአመንክሙኒ ብየ
ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ወፃእኩ ።
እናንት ወዳችሁኛልና አምናችሁብኛልምና እኔ ከእ
ግዚአብሔር እንደ ወጣሁ ።

፳፰ ወመጻእኩ ውስተ ዓለም ።
፳፰ ከእግዚአብሔር አብ አካል ዘእምአካል
ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልጄ ወደዚህ ዓለም ፡
መጣሁ ።
ወካዕበ እኅድጎ ለዓለም ወአሐውር ኀበ አብ
ዳግመኛ ሰውን ተለይቼው ወደ አብ እሄዳለሁ ፡
ፀሞት መለየቱን በረድኤት ስመለየቱ ካዕበ አለ ። አን
ድም በዕርገት መለየቱን በሞት ለመለየቱ ካዕበ አለ ።

፳፱ ወይቤልዎ አርዳኢሁ ይእዜሰ ገሃደ ተና
ገርከነ ።

፳፱ ደቀ መዛሙርቱም ዛሬ ግን ገልጸህ
ነገርከን ።
ወአልቦ ዘመሰልከ ወኢምንተኒ ።
ምንም ምን ሰውረህ የነገርከን ነገር የለም ።

፴ ወይእዜሰ አእመርነ ከመ ዙሎ ተአምር
አንተ ።

፴ ዛሬ ግን ሁሉን እንድታውቅ ዐወቅን ።
ወኢትፈቅድ ይንግርከ መኑሂ ።
ማንም ማን ሊነግርህ አትሻም አሉት ።
ወበእንተ ዝንቱ ነአምር ከመ እምኀበ እግዚአብ
ሔር ወፃእከ ።
ከእግዚአብሔር አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእ
ምባሕርይ እንደተወለድህ በዚህ እናውቃለን ።

፴፩ ወአውሥአ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ
ይእዜሰኬ አእምሩ ወእመኑ ።

፴፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መለሰላቸው
አላቸውም አሁን ዕወቁ እመኑ ።

፴፪ ናሁ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ ።
፴፪ እነሆ ጊዜው እንደደረሰ ።
ወበጺሖሂ ከመ ዙልክሙ ትዘረው ለለ፩ዱ ፩ዱ
ውስተ መካኑ ።
በደረሰም ጊዜ ሁላችሁ እያንዳንዳችሁ እንድት
በተኑ ዕወቁ አላቸው ።
ወተኃድጉኒ ባሕቲትየ ።
ብቻየን ትተውኛላችሁ ።
ወባሕቱ ኢኮንኩ አነ ባሕቲትየ ።
እኔ ግን ብቻዬን አይደለሁም ።
እስመ አብ ምስሌየ ውእቱ ።
አብ በኔ ህልውና ነውና ።

፴፫ ወዝንቱ ውእቱ ዘነገርኩክሙ ከመ ብየ
ሰላመ ትርከቡ ።

፴፫ በኔ አንድነትን ታገኙ ዘንድ የነገርኳችሁ
ይህ ነው ።
ወበዓለምሰ ሕማመ ትረክቡ ።
በዓለም ግን መከራን ትቀበላላችሁ ።
ወባሕቱ ጽንኡ እስመ አነ ሞዕክዎ ለዓለም ።
ነገር ግን እኔ ድል ነሥቸለሁና ድል ንሡ ። ድል
ነሥቶ ድል ንሡ አለ ድል የተነሣን ጾር ቤት ሳት
ቀር ትማርከዋለችና ።

ዘከመ ጸለየ ኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፲፯ ።

፩ ወዘንተ ነገረ ተናጊሮ እግዚእ ኢየሱስ
አንሥአ አዕይንቲሁ ውስተ ሰማይ ።

፩ ይህን ተናግሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ዓይኑን ወደ ሰማይ አቀና ። ሐተታ እስካሁን
ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ይነጋገር ነበር እንግዲህ ወዲህ
ግን ከአብ ጋራ ለመነጋገር ።
ወይቤ አባ በጽሐ ጊዜሁ ከመ ትስብሖ ለወልድከ።
አባቴ ሆይ ልጅህን ትገልጸው ዘንድ ጊዜው ደረሰ ።
ወከመ ወልድከኒ ይስብሕከ ።
ልጅህም ደግሞ ያመሰግንህ ዘንድ ።

፪ በከመ አኰነንኮ ላዕለ ኵሉ ዘሥጋ ወነ
ፍስ ከመ የሀቦሙ ሕይወተ ዘለዓለም ለኵሉ ወሀ
ብካሁ ። ማቴ. ፳፰፡ ፲፰ ።

፪ በሀብት ሰበህ በረድኤት አቅርበህ ለሰጠ
ኸው ለምእመናን የዘለዓለም ሕይውት የሚገኝበ
ትን ይሰጣቸው ዘንድ ። የዘለዓለም ሕይወት

የሚገኝበትን ሃይማኖት ያስተምራቸው ዘንድ በሥጋዊ በነፍሳዊ ሁሉ ላይ እንዳሠለጠንከው መጠን ልጅህም ይገልጽልህ ዘንድ ።

፫ ወዛቲ ይእቲ ሕይወት ዘለዓለም ከመ ያእምሩ ኪያከ ለ፩ ዘበአማን አምላክ ጽድቅ ባሕቲትከ ።

፫ የዘለዓለም ሕይወት የሚገኝበት ሃይማኖትም
አንተ ብቻ የባሕርይ አምላክ እንደሆንክ ።
ወዘፈነውኮ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድከ ።
የላከኸው ኢየሱስ ክርስቶስም የባሕርይ አምላክ እንደሆነ ያውቁ ዘንድ ነው ። እንዲያውቁ መሆን ነው ቢያውቁ በጐ ነው ቢያውቁ የዘለዓለም ሕይወት የሚገኝባት ሃይማኖት ይህች ናት ።

፬ አንሰ ሰባሕኩከ ቢዲበ ምድር ፈጺምየ ግብረ ዘወሀብከኒ ከመ እግበር ።

፬ እሠራው ዘንድ ግንዘብ ያደረግህልኝን ሥራ ሠርቼ ገለጽሁህ ።

፭ ወይእዜኒ አንተ አባ ሰብሐኒ ቢሰብሐትየ ዘሀሎ ኀቤከ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ።

፭ አባት ሆይ አሁንም አንተ ዓለም ሳይፈጠር ካንተ ዘንድ ባለ ጌትነቴ ግለጸኝ ፡ አንድም በስብሐቲከ ዘሀሎ ኀቤየ ይላል ዓለም ሳይፈጠር ከኔ ዘንድ ባለ ጌትነትህ ግለጸኝ ።

፮ ወነገርኩ ስመከ ለሰብእ ለእለ ወሀብከኒ እምዓለም ።

፮ በሀብት ሰበህ በረድኤት አቅርበህ ለሰጠኸኝ ለምእመናን አባትነትህን ነገርኳቸው ።
እስመ ዚአከ እሙንቱ ።
ያንተ ገንዘቦች ናቸውና ።
ወሊተ ወሀብከኒዮሙ ።
ለኔም ሰጠሀቸው ።
ወዓቀቡ ቃለከ ።
ሕግህንም ጠበቁ ።

፯ ወይእዜኒ አእመሩ ከመ ኵሉ ዘወሀብከኒ እምኀቤከ ውእቱ ።

፯ የሰጠኸኝ ሁሉ ካንተ እንደሆነ የነገርኳቸው ሁሉ ካንተ እንደተገኘ ዐውቀዋልና ።
እስመ ወሀብክዎሙ ቃለ ዘወሀብከኒ ።
የሰጠኸኝን ነገር ሰጥቻቸዋለሁና ማለት የነገርከኝን አስተምሬያቸዋለሁና ።

፰ ወእሙንቱኒ ነሢኦሙ አማን አእመሩ ከመ እምኀቤከ ወፃእኩ ወአምኑ ከመ አንተ ፈነውከኒ ።

፰ እርሳቸውም የነገርኳቸውን ትምህርት ተቀብለው ከአንተ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልጄ እንደመጣሁ ባንተ ፈቃድ ሰው እንደሆንሁ አውቀው አምነዋል ።

፱ ወአንሰ በእንቲአሆሙ እሰእል ።
፱ እኔ ስለርሳቸው እለምንሃለሁ ።
ወአኮ በእንተ ዓለም ዘእስእለከ አላ በእንተ እለ ወሀብከኒ ።
የምለምንህ በሀብት ሰበህ በረድኤት አቅርበህ ለሰጠኸኝ ለነህ ነው እንጂ ለሌላው ያይደል ፤
እስመ እሊአከ እሙንቱ ።
ያንተ ገንዘቦች ናቸውና ።

፲ ወኵሉ ዘዚአየ ዚአከ ውእቱ ወዘዚአከኒ ዚአየ ውእቱ ።

፲ የኔ ገንዘብ ሐዋርያት ፡ ያንተ ገንዘብ ነቢያት ናቸው ፡ አንድም የኔ ገንዘብ ሐዋርያት ያንተ ገንዘቦችህ ናቸው ወዘዚአከኒ ዚአየ ውእቱ ።
ያንተ ገንዘብ ነቢያትም የኔ ገንዘቦች ናቸው ።
ወተሰባሕኩ ቦሙ ።
በርሳቸው ተገለጽኩ በርሳቸው ሥጋ ከበርኩ ።

፲፩ ወኢይሄሉ እንከ ውስተ ዓለም
፲፩ ከእንግዲህ ወዲህ በዓለም አልኖርም ።
ወእሙንቱሰ ውስተ ዓለም ይሄልዉ ።
እርሳቸው ግን በዓለም ይኖራሉ ።
ወአንሰ ኀቤከ እመጽእ ፡
እኔ ግን ወዳንተ እመጣለሁ ፡
አባ ቅዱስ ዕቀቦሙ በስምከ ለእለ ወሀብከኒ ፤
ልዩ አባት ፡ ክቡር አባት ፡ አባት የሌለህ አባት በሀብት ሰብህ በረድኤት አቅርበህ የሰጠኸኝን ምእመናንን በስምህ ጠብቃቸው ።
ከመ ይኩኑ ፩ደ ብነ ከማነ ከመ ፩ዱ ንሕነ ።
እኛ በባሕርይ አንድ እንደሆነ እርሳቸውም በጸጋ አንድ ይሆኑ ዘንድ ፡

፲፪ እመሰ ሀሎኩ አነ ውስተ ዓለም ዓቀብክዎሙ በስምከ ለእለ ወሀብከኒ ፡ ዮሐ፣ ፲፰፡፱ መዝ፡ ፵፲፡፲ ።

፲፪ በሀብት ሰበህ በረድኤት አቅርበህ የሰጠኸኝኒ በዚህ ዓለም ሳለሁ በስምህ ጠበቅኋቸው ።
ናሁ ዓቀብክዎሙ ።
አጽንቼ ጠበቅኋቸው ።
ወኢትኃጕለ ፩ሂ እምኔሆሙ ዘእንበለ ወልደ ኃጕል ።
ጥፋት ከሚገባው ከይሁዳ በቀር ከእርሳቸው አንድ ስንኳ የጠፋ የለም ።
ከመ ይትፈጸም ቃለ መጽሐፍ ።
መጽሐፍ ወይጥፋእ እምድር ዝክሩ ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ።

፲፫ ወይእዜሰ ባሕቱ እመጽእ ኀቤከ ።
፲፫ ዛሬ ግን ወዳንተ እመጣለሁ ።
ወለእሉሰ አኃድጎሙ ውስተ ዓለም ።
እርሳቸውን ግን በዓለም እተዋቸዋለሁ ።
ወዘንተ እነግር ውስተ ዓለም
ይኸንንም በዓለም እናገራለሁ
ከመ ይኩን ፍሥሐየ ፍጹመ በላዕሌሆሙ
ደስታዬ በርሳቸው ፍጹም ይሆን ዘንድ ማለት ፈጽሞ ደስ ይላቸው ዘንድ ።

፲፬ ወአንሰ ፈጺምየ ወሀብክዎሙ ቃለከ ።
፲፬ ሕግህን ፈጽሜ ነገርኋቸው ።
ወዓለምሰ ጸልኦሙ ።
ሰው ግን ይጸላቸዋል ።
እስመ ኢኮኑ እሙንቱ እምዓለም ።
እርሳቸው ከዓለም አይደሉምና
በከመ ኢኮንኩ አነ እምዓለም
እኔ ከዓለም ወገን እንዳይደለሁ ከዓለም እንዳልተገኘሁ ።

፲፭ አኮ ዘእስእለከ ከመ ትንሥኦሙ እምዓለም።
፲፭ ዛሬስ ከዚህ አኦርን ሞት ይካስስብናል እንዳይሉት የምለምንህ በሞት ትወስዳቸው ዘንድ አይደለም ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ ትዕቀቦሙ እምእኩይ ። ከሞት ትጠብቃቸው ዘንድ ነው እንጂ አብ የማያውቅ ሁኖ አይደለም በአብ ለሐዋርያት ለመንገር ነው ። ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ባለ ጊዜ ወልድ ልጅነቱን የማያውቅ ሁኖ እንዳይደለ በወልድ ለዮሐንስ ለመንገር እንደሆን ።

፲፮ እስመ እሙንቱ ኢኮኑ እምዓለም ።
፲፮ እሳቸው ከዓለም ወገን አይደሉምና ።
በከመ ኢኮንኩ አነ እምዓለም
እኔ ከዓለም እንዳልተገኘሁ ።

፲፯ ቀድሶሙ በጽድቅከ ።
፲፯ በጽኑ ቀጠሮህ አጽናቸው ።
እስመ ጽድቅ ውእቱ ቃልከ ።
ቀጠሮህ ጽኑ ነውና ። አንድም በአካላዊ ቃልህ አከብራቸው ቃልህ አካላዊ ነውና ።

፲፰ በከመ አንተ ፈነውከኒ ውስተ ዓለም ኪያየ።
፲፰ አንተ እኔን ወደዓለም እንደ ላከኸኝ ።
ከማሁ አነኒ ፈነውክዎሙ ውስተ ዓለም ።
እኔም ወደዓለም ላክኋቸው ።

፲፱ ወበእንቲአሆሙ አነ እቄድስ ርእስየ ።
፲፱ ስለርሳቸው ተሰቅዬ ነፍሴን ከሥጋዬ እለያለሁ ። አንድም ስለርሳቸው ራሴን አከብራለሁ።
ከመ ይኩኑ እሙንቱሂ ቅዱሳነ በጽድቅ ።
በውነት ንጹዳን ከቡራን ይሆኑ ዘንድ ።

፳ ወአኮ በእንተ እሉ ባሕቲቶሙ ዘእስእለከ።
፳ የምለምንህ ስለነሱ ብቻ አይደለም ።
አላ በእንተሂ እለ የአምኑ ብየ በቃሎሙ ።
ከርሳቸው ተምረው ስለሚያምኑ እስከ ምጽአት ድረስ ስለሚነሡ ምእመናንም ነው እንጂ ።

፳፩ ከመ ይኩኑ አሐደ ኵሎሙ ከማነ ከመ ፩ ንሕነ ።

፳፩ ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ እኛ በባሕርይ አንድ እንደሆን
በከመ አንተ አብ ብየ ።
አባት ሆይ አንተ በኔ ህልው እንደሆንክ ።
ወአነሂ ብከ ።
እኔም ባንተ ህልው እንደሆንኩ ።
ከመ ይኩኑ እሙንቱሂ ብነ ከማነ ከመ ፩ ንሕነ ።
እኛ በባሕርይ አንድ እንደሆን እርሳቸው በጸጋ አንድ ይሆኑ ዘንድ ።
ከመ ይእመን ዓለም ከመ አንተ ፈነውከኒ ።
ባንተ ፈቃድ ሰው እንደሆንኩ ዓለም ያምንዘንድ ።
፳፪ ወአነሂ ወሀብክዎሙ ቃለከ ዘወሀብከኒ ።

፳፪ እኔም የሰጠኸኝን ሰጠኋቸው ማለት የነገርከኝን ነገርኳቸው ።
ከመ ይኩኑ አሐደ ከማነ በከመ አሐዱ ንሕነ ።
እኛ በባሕርይ አንድ እንደሆን በጸጋ አንድ ይሆኑ ዘንድ ።

፳፫ ወአነሂ ቦሙ ።
፳፫ እኔም አድሬባቸው እኖራለሁ ።
ወአንተሂ ብየ ።
አንተም በኔ ህልው ሁነህ እንድትኖር ።
ከመ እሙንቱሂ ይኩኑ ፍጹማነ በአሐዱ ።
በአሐዱ ያለውን ፍቅር ብሎታል ሊቁ በፍቅር አንድ ይሆኑ ዘንድ ።
ከመ ይእመን ዓለም ከመ አንተ ፈነውከኒ ።
አንተ እንደ ላከኸኝ ባንተ ፈቃድ ሰው እንደሆንኩ ዓለም ያውቅ ዘንድ ።
ወአፍቀርከዎሙ አነ በከመ አንተ ኪያየ አፍቀርከኒ።
እኔን እንደወደድኸኝ ወደድኋቸው ሙት ተሰቀል እንዳልኸኝ ሙቱ ተሰቀሉ አልኳቸው ።

፳፬ አባ እለሰ ወሀብከኒ እፈቅድ ። ከመ የሀልዉ ኀበ ሀሎኩ አነ ምስሌየ ከመ ይርአዩ ስብሐተ ዘወሀብከኒ ።

፳፬ አባት ሆይ የሰጠኸኝ ምእመናን የሰጠኸኝን ክብር ያዩ ዘንድ ከኔ ጋራ እኔ ካለሁበት ሊኖሩ እወዳለሁ ። አንድም የሰጠኸኝን ክብር ይወርሱ ዘንድ ።
እስመ አንተ አፍቀርከኒ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ።
ዓለም ሳይፈጠር ወደኸኛልና ።

፳፭ አባ ጻድቅ ወዓለምስ ኢያእመረከ ።

፳፭ የባሕርይ አምላክ አባቴ ሰው አላወቀህም

ወእንሰ ባሕቱ አእመርኩከ ።
እኔ ግን አውቄሃለሁ ።
ወእሙንቱስ አእመሩከ ከመ አንተ ፈነውከኒ ።
እርሳቸውም ባንተ ፈቃድ ሰው እንደሆንኩ ዐውቀዋል ።

፳፮ ወነገርክዎሙ ስመከ ።

፳፮ አባትነትኽን ነገርኋቸው ስምህን አስታወቅኋቸው ።
ወዓዲ እነግሮሙ ።
ዳግመኛም እነግራቸዋለሁ ።
ከመ የሃሉ ኀቤሆሙ ፍቅር ዘአፍቀርከኒ ።
አንተ ያፈቀርከኝ ፍቅር በርሳቸው ጸንቶ ይኖር ዘንድ ።
ወአነሂ እሄሉ ቦሙ ።
እኔም አድሬባቸው እኖራለሁ ።

ዘከመ ጸለየ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ።

ምዕራፍ ፲፰ ።

፩ ወዘንተ ብሂሎ ወፅአ እግዚእ ኢየሱስ ምስለ አርዳኢሁ ማዕዶተ ቄድሮስ ፈለገ አርዝ ፪ ነገ. ፲፭ ፳፫ ፤ ማቴ. ፳፮ ፤ ማቴ ፳፮ ፴፮ ፤ ማር. ፲፬ ፡ ፴፪ ። ሉቃ. ፳፪ ፡ ፴፱ ።

፩ ማዕዶትና ፈለግ ቄድሮስና አርዝ አንድ ወገን ነው ። ይህን ተናግሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንዙን ተሻግሮ ያለውን ዛፍ አልፎ ወዳስውዱር ገባ ። አንድም ዘይቤውን ለማውጣት ዛፉን አልፎ ያለውን ወንዝ ተሻግሮ ያለውን ዛፍ አልፎ ወዳለው ዱር ገባ ። ማቴዎስ ጌቴሴማኒ ፣ ሉቃስ ደብረ ዘይት ይላል ፥ ከዚህ እንዲህ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ። አንድ ወገን ነው እንዳጠናቅር ገብርኤል እንደ ጐንደሮች ጊዮርጊስ አንድም እንደሉቃስ ዓሥራ አንዱን ይዞ ደብረ ዘይት ይገባል ስምንቱን በደብረ ዘይት ትቶ እንደ ማቴዎስ ሦስቱን ባለሟሎቹን አስከትሎ ጌቴሴማኒ ገብቷል ። መጠነ ሙጋረ እብን ይላል ደንጊያ ወርውሮ እስከ ሚያርፍበት ሂዶ ግምባሩን ምድር አስነክቶ ሰግዶ ጸሎቱን ፈጽሞ ተመልሶ ስምንቱን ከደብረ ዘይት ሦስቱን ባለሟሎቹን ከጌቴሴማኒ ይዞ እንደ ዮሐንስ ከዚህ ገብቷል ።
ወቦ ህየ ዐጸደ ሐምል ፣
ከዚያ ያታክልት ቦታ አለ ።
ወቦአ እግዚእ ኢየሱስ ውስቴታ ምስለ አርዳኢሁ ።
ጌታም ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ከዚያ ገባ ።

፪ ወየአምሮ ይሁዳ ዘያገብኦ ለውእቱ መካን ።

፪ የሚያሲዘው ይሁዳ ያን ቦታ ያውቀው ነበር ።
እስመ ብዙኃ ጊዜ ይትጋባእ እግዚእ ኢየሱስ ህየ ምስለ አርዳኢሁ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ሥፍራ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ብዙ ጊዜ ቆይታ ያደርግ ነበርና ።

ዘከመ አግብኦ ይሁዳ ለኢየሱስ ወዘከመ አኀዝዎ ለኢየሱስ ።

፫ ወነሥኦሙ ይሁዳ ለሠገራተ ሰጲራ እምኀበ ሊቃነ ካህናት ወፈሪሳውያን ፣ ማቴ. ፳፮ ፡ ፵፯ ። ማር. ፲፬ ፡ ፵፫ ሉቃ. ፳፪ ፡ ፵፯ ።

፫ ይሁዳም ከካህናት አለቆችና ከፈሪሳውያን ። ሰጲራ የሚባል ጭፍራ ተቀብሎ ።
ወነሥአ ረድኤተ ወዓልያኒሆሙ
ብላቴኖቻቸውን ረዳት አክሎ መጣ ሐተታ እምስት ገበያ ሰው ይከተለዋል አግባ መልስ ብሎ ቢጣላንስ ብለው ከጲላጦስ ያመጡት ፣ እሱ ከርሳቸው ተቀብሎ ይዞ ይመጣል ።
ወሖረ ህየ በመሐትወ ጽጕ ወምናት ።
ፋኖስ የጭራሮ መብራት አስይዞ ፣ አንድም ፋኖስ የሚባል ማብሪያ ይዘው ነፋስ የማያስገባ ብርሃን የማይከለክል ነው ይህን ሁሉ ምን ያሻቸዋል ምልአተ ወርህ አይደለምን ቢሉ የጨረቃ ብርሃን እንደ ፀሐይ ብርሃን መልክ ለይቶ አያሳውቅምና ።
አንድም ያለንበት ቦታ ዱር ነው ብርሃን አያስገባምና ይህ ሁሉ አይደለም መዓልት ብርሃኑዋን እንደ ነሳች ሌሊትም ብርሃኑዋን ነስታ ነበርና ።
ወበንዋየ ሐቅል ።   ሾተል ጐመድ ይዞ ።

፬ ወአእሚሮ እግዚእ ኢየሱስ ኵሎ ዘይበጽሕ ላዕሌሁ ወፅአ አፍአ ኀቤሆሙ ።

፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የሚመጣበትን ሁሉ ማለት ሊይዙት እንደመጡ ዐውቆ ካለበት ቦታ እርሳቸው ወዳሉበት ወጣ ። ሳያውቅ በድንገት ያዝነው እንዳይሉ እንዳይቀርለት ያውቃልና እንዳልፈራ ለማጠየቅ ። አንድም አፍቅሮ ጸላእት እሾህ እንዳያወጋቸው ዕንቅፋት እንዳይመታቸው ። አንድም ኀድግዎሙ ለእሉ ይሑሩ ለማለት ።
ወይቤሎሙ መነ ተኀሥሡ ።
ማን ትሻላችሁ አላቸው ።
፭ ወአውሥኡ ፡
፭ መለሱ ።
ወይቤሉ ኢየሱስሃ ናዝራዊ ።
የናዝሬቱ ኢየሱስን ነው አሉት
ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አነ ውእቱ ።
ኢየሱስም እኔ ነኝ አላቸው ።
ወሀሎ ይሁዳኒ ዘያገብኦ ይቀውም ምስሌሆሙ ።
ያስያዘው ይሁዳም ከርሳቸው ጋራ ቁሞ ነበር ።

፮ ወሶበ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ገብኡ ድኅሬሆሙ ወወድቁ ዲበ ምድር ።

፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜም ወደኋላቸው ተመልሰው ወደቁ ። ወደ ኋላ የወደቁት ድቀት ጽኑ ነው ጽኑ ድቀት እንዳለባቸው ለማጠየቅ ። አንድም ጥፋታቸው በኋላ ዘመን ነውና በሥጋቸው ባርባ ዘመን በጥጦስ በነፍሳቸው በገሃነም ። አንድም ወወድቁ ታሕተ ጽላሎቱ ያለው ትን ቢት ሊፈጸም ።

፯ ወእምዝ ካዕበ ተስእሎሙ ወይቤሎሙ መነ ተኀሥሡ ።

፯ ደግሞም ጠየቃቸው እንዲህ ሲል ማን ትሻላችሁ ።
ወይቤልዎ ኢየሱስሃ ናዝራዌ ።
የናዝሬቱን ኢየሱስን ነው አሉት ።
፰ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።

፰ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎሙ እኮኑ እቤለክሙ አነ ውእቱ ።
እኔ ነኝ አላልኋችሁምን ።
ወእመሰ ኪያየ ተኀሥሡ ኅድግዎሙ ለእሉ ይሑሩ።
የምትሹ እኔን ከሆነስ እነዚህን ተዋቸውና ይሂዱ ።

፱ ከመ ይብጻሕ ቃል ዘይቤ እለሰ ወሀብከኒ ኢተኀጕለ ወኢአሐዱሂ እምኔሆሙ ። ዮሐ. ፲፯፡፲፪።

፱ ከሰጠኸኝ አንዱ ስንኳ አልጠፋም ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ።

፲ ወቦ መጥባሕት ለስምዖን ጴጥሮስ ።
፲ ለጴጥሮስ በጉን የበሉበት ሾተል ነበረው ።
ወመልሐ መጥባሕቶ ወዘበጦ ለገብረ ሊቀ ካህናት።
ሾተሉን መዞ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መታው ።
ወመተረ እዝኖ ዘየማን ።
ቀኝ ጆሮውን ቆረጠው ። ንዝብጦሙ ንዝብጦሙ ተባብለዋል በሉቃስ ። አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት አብሮ ለመሞት እንጂ ነው ። እንበላቸው እንበሳቸው ተባብለዋል ቅዱስ ጴጥሮስ ፈጣን ነውና ሾተሉን መዞ መታው ቀኝ ጆሮውን ቆረጠው ። ከመታው አንገቱን አይለውምን ቢሉ የካህን እጅ አያቀናምና ሳንገቱ ያለው ለጆሮው ሆነ አንድም አንገቱን መቶት ቢሆን ይሞታል የጌታም ሞት በርትዕ ነው በተባለ ነበርና ጆሮውንሳ ቢሉ ወእሐየዎ ይላል ቀጥሎለታል ። ስለምን በጆሮው ምትረትን አዘዘባት ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ትንቢት ወይእቲ እዝን እንተ ኢትሰምዖ ለውእቱ ነቢይ ለትትቀረጽ ተብሎ ተነግሯል ። ምሳሌም ወለእመ አጥረይከ ገብረ ዕብራዌ ስድስተ ዓመተ ቅንዮ ወበሳብእ ዓም አግዕዞ በከንቱ ትላለች እሪት ፡ እርሱ ግን የመቤቴ እንጀራዋ ወጪ ጣፍጦኛል የጌታዬ ባሕርይ ተስማምቶኛል ነፃ መውጣቱ ይቅርብኝ ስገዛ እኖራለሁ ቢል ከቤተ መቅደስ ከመድረኩ አስተኝቶ ጆሮውን ተልትሎ አፍንጫውን ሸንቁሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ይግዛው ትላለች ። ጌታም በስድስተኛው ሺህ ከዲያብሎስ ተቀንዮ ነፃ ላወጣችሁ መጥቼ ነበር አይሆንም ካላችሁ በሥጋችሁ ቄሣር በነፍሳችሁ ዲያብሎስ ይሠልጥንባችሁ ለማለት ። ቀኙቱ መሆንዋ ግራይቱ አለመሆንዋ ስለምን ነው ቢሉ ከነገደ ይሁዳ የተወለደ ቀኝ ቀኝ አካሉን ተቀብቶ መንግሥትን ከነገደ ሌዊ የተወለደ ቀኝ ቀኝ አካሉን ተቀብቶ ክህነትን እጅ ያደርግ ነበር መንግሥትንም ክህነትንም እንዳሳለፈባቸው ለማጠየቅ ። ወስሙ ለውእቱ ገብር ማልኮስያም ባሪያ ማልኮስ ይባል ነበር ። እግዚእ ወገብር ማለት ነው ፣

፲፩ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ለጴጥሮስ አግብእ ለመጥባሕትከ ውስተ ቤታ ።

፲፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሾተልክን ወደአፎት ቀጣህን ወደ ትዕግሥት መልስ አለው። ጽዋዓ ዘወሀበኒ አቡየ ኢየኀድግ ዘእንበለ እስተይ አባቴ የሰጠኝን ጽዋ ሳልጠጣ አልተወውም ማለት ባባቴ ፈቃድ የሚሆነውን ሞት እሞታለሁ ።

ዘከመ ቆመ ኢየሱስ ማእከለ ዐውድ ።

፲፪ ወአኀዝዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ሰገራተ ሰጲራ።
፲፪ ሰጲራ የሚባል ጭፍራ ።
ወሊቀ ዓሠርቱ ምእት ።
የመቶ አዝማች ።
ወወዓሊሆሙ ለአይሁድ ።
የአይሁድም ብላቴኖች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘው ።
ወሐመይዎ ። አሰሩት ።

፲፫ ወወሰድዎ ኀበ ሐና ቀዲሙ ሉ.ቃ.፫፡ ፪።
፲፫ አስቀድሞ ከሐና ዘንድ ወሰዱት ።
እስመ ሐሙሁ ውእቱ ለቀያፋ ሊቀ ካህናት ዘዕብሬቱ ይእቲ ዓመት ።
ሹመቱ በዚያ ወራት ለሚሆን ለሊቀ ካህናቱ ለቀያፋ አማች ነበርና ። ማቴ አስቀድሞ ከሐና ወሰዱት ይላል ። ከዚህ እንዲህ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም አስቀድሞ ከቀያፋ ወስደውታል ምንስ እኔ ሹም ብሆን ሽማግሌ ሳለ ከርሱ ውሰዱት ብሏቸዋል ከሐና ወስደውታል የኋለኛውን ዮሐንስ የፊተኛውን ማቴዎስ ይጽፋሉ ። አንድም እንደ ማቴዎስ ነው አስቀድሞ ከሐና ወስደውታል ምንስ እኔ ሽማግሌ ብሆን ሹሙ ሳለ ከርሱ ዘንድ ውሰዱት ብሏቸው ከቀያፋ ወስደውታል የፊተኛውን እንደ ዮሐንስ የኋለኛውን እንደ ማቴዎስ ተናገሩ ። ነገር እንደ ዮሐንስ ነው ። አንድም እንደ ጎንባሲት

ያለች ደጅ አለቻቸው አንድ ጊዜ ባንዱ ሲያገቡት አንድ ጊዜ ባንዱ ሲያወጡት ሲያመላልሱት አድረዋል አንዱ ላንዱ ቅድሙ ነውና ቅድመ ኀበ ቀያፋ ቅድመ ኀበ ሐና አለ ።

፲፬ ወቀያፋሰ ውእቱ ዘአምከሮሙ ለአይሁድ ወይቤሎሙ ይኄይስነ ንቅትል አሐደ ብእሴ እምይትኀጐል ኵሉ ሕዝብ ዮሐ ፣ ፲፩፣፵፱ ።

፲፬ ያተርካል ቀያፋም ሰው ሁሉ በርሱ አምኖ ሲጐዳ አንድ ሰው ብንገድል ይሻለናል ብሎ አይሁድን የመከራቸው ነው ።

በእንተ ክህደተ ጴጥሮስ ።

፲፭ ወተለውዎ ለእግዚእ ኢየሱስ እምርጉቅ ስምዖን ጴጥሮስ ወካልዕኒ ረድእ ።

፲፭ ዮሐንስና ስምዖን ጴጥሮስ ጌታን ርቀው ተከተሉት ።
ወውእቱሰ ረድእ ዘልሙድ በኀበ ሊቀ ካህናት ።
ያም ደቀ መዝሙር ከሊቀ ካህናቱ የለመደ ነው ፣ ባሣ ቀረጥ ምክንያት ፡ አንድም ከቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥት ይወለዳልና ።
ወቦአ ምስለ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ዐጸደ ሊቀ ካህናት ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትሎ ከሊቀ ካህናቱ ቦታ ገባ ።

፲፮ ወጴጥሮስሰ ቆመ አፍአ ኀበ ኆኅት ። ማቴ፣ ፳፮፣፶፰ ማር፣ ፲፬፣፶፬ ሉቃ፣ ፳፪ ፶፭ ።

፲፮ ጴጥሮስ ግን ተከልክሎ እውጭ ቁሞ ነበር ።
ወወፅአ ዝኩ ረድዕ ዘልሙድ በኀበ ሊቀ ካህናት ወተናገራ ለአፃዊት ወአብኦ ለስምዖን ጴጥሮስ ፣ ዮሐንስ ወጥቶ ከበረኛዪቱ ተነጋግሮ ጴጥሮስን አለ ገባው ጠባቂው ወንድ አይደለምን ቢሉ ከጭፍራው ድፋት ያለው ነውና ጩኸት ቢሰማ አስጠብቃት ሄዷል ይህች ልጅ ልጁም እንደሆነች አልታወቀም ።

፲፯ ወትቤሎ ይእቲ ዓመት አፃዊት ለጴጥሮስ አንተኑ እምአርዳኢሁ ለውእቱ ብእሲ ኦንተ ።

፲፯ ያችም ብላቴና ጴጥሮስን አንተም ከዚያ ሰው ደቀ መዛሙርት ወገን ነህ አለችው ።
ወይቤላ ውእቱኒ ኢኮንኩ ።
እርሱም አይደለሁም አላት ።

፲፰ ወሀለዉ ያቀውሙ እግብርቲሆሙ ወወዓልያኒሆሙ ለአይሁድ ወይበቁጹ እፍሐመ ወይስሕኑ

፲፰ ብላቴኖቻቸው ተቀምጠው እሳት እየሜሩ ይሞቁ ነበር ። ወትቀውም ንግሥት በየማንክ እንዲል ።
እስመ ብዙኀ ቍሩ ለይእቲ ሌሊት ።

በዚያ ሌሊት ብርድ ጸንቶ ነበርና ዐእተ ክረምት ነውና ።
አንድም ወትከውን አሐቲ ዕለት ቍረ ወበረደ ያለው ሊፈጸም ብርድ ጸንቶ ነበር ።
ወይቀውም ጴጥሮስኒ ወይሰሐን ምስሌሆሙ ።
ጴጥሮስም ከርሳቸው ጋራ ተቀምጦ ይሞቅ ነበር ።

ዘከመ ተስእልዎ አይሁድ ለኢየሱስ ።

፲፱ ወተስእሎ ሊቀ ካህናት ለእግዚእ ኢየሱስ በእንተ አርዳኢሁ ።

፲፱ ሊቀ ካህናቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ ደቀ መዛሙርቱ ማለት ደቀ መዛሙርትህ ምን እያሉ ያስተምራሉ ።
ወበእንተ ትምህርቱ ።
አንተስ ምን ብለህ ታስተምራለህ ብሎ ጠየቀው አንድም ። ሐዋርያት ሰብዓ አርድዕት እያልክ መሾምህ በምን ነገር ነው ብሎ ጠየቀው ።

፳ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፳ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ አንሰ ክሡተ ተናገርኩ ውስተ ዓለም ።
እኔ በዚህ ዓለም ገልጬ አስተማርኩ ።
ወበኵሉ ጊዜ መሐርኩ በምኵራብ ወበቤተ መቅደስ ኀበ ይትጋብኡ ኵሎሙ አይሁድ ።
አይሁድ በሚሰበሰቡበት በምኵራብ በቤተ መቅደስ አስተማርኩ ።
ወአልቦ ዘተናገርኩ ጽሚተ ወኢምንተኒ ።
ምንም ምን ሰውሬ የተናገርኩት የለም ።

፳፩ ለምንት እንከ ትሴአለኒ ሊተ ተሰእሎሙ ለእልክቱ እለ ሰምዑኒ ዘተናገርክዎሙ ።

፳፩ የነገርኳቸውን የሰሙትን እሊህን ጠይቃቸው እንጂ እኔን ምን ትጠያቀኛለህ ።
እስመ እሙንቱ የአምሩ ዘተናገርኩ አነ ።
እኔ የተናገርኩትን እርሳቸው ያውቃሉና ።

፳፪ ወዘንተ ብሂሎ ጸፍአ መልታሕቶ ለእግዚእ ኢየሱስ እምእለ ይቀውሙ ወዓልት ።
፳፪ ይህን በተናገረ ጊዜ ይህን ከተናገረ በኋላ ከቆሙት ብላቴኖች አንዱ ጌታን በጥፊ መታው ፣ መጻጉዕ ነው ።
ወይቤሎ ከመዝኑ ትትዋሥእ ለሊቀ ካህናት ።
ለሊቀ ካህናቱ እንዲህ አኩል ትመልስለታለህን ብሎ ።

፳፫ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ማቴ. ፳፮ ፣ ፶፯ ። ማር. ፲፬ ፣ ፷፭ ። ሉቃ. ፳፪ ፶፬ ።

፳፫ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ እመሰ እኩየ ነበብኩ ስምዓ ኩን ላዕሌየ ።
ክፉንስ ተናግሬ እንደሆነ መስክርብኝ ።

ወእስተዋድየኒ በእንተ እኩይ ፡፡
ክፉ ስለተናገርኩ አሳጣኝ አጣላኝ አካስኝ ፡፡
ወእመሰ ሠናየ ነበብኩ ለምንት እንከ ትዘብጠኒ ፡፡
በጐ ነገር ብናገር ግን ለምን ትመታኛለህ አለው ፤ ጌታ በትሩን ተስቅቆት አይደለም ከዳኛ ፊት መማታት አይገባም ለማለት ሥርዓት ለማስተማር ነው እንጂ ምንም ቢሆን ነኝ ብሏልና ፤
አንድም ወይቤሎ እመሰ እኩየ ነበብኩ ብለህ መልስ ተንሥእ ወጹር ዓራተከ ብዬ ከደዌህ ባልፈውስህ መስከርብኝ አጣላኝ በእንተ እኩይ ከደዌህ ስላል ፈወስኩህ ፤ ወእመሰ ፤ ከደዌህ ስለፈውስኩህ ግን ለምን ትመታኛለህ የበጐነት ወረታ ከፋት ነውን አለው ፡፡ ገጸ መለኮቱን የመታበት እጁ ስሉ ደርቆ ቀርቷል ፡፡

፳፬ ወፈነዎ ሐና ሕሙዮ ኀበ ቀያፋ ሊቀ ካህናት
፳፬ እንደታሰረ ወደሊቀ ካህናቱ ወደቀያፋ ላከው
፳፭ ወሀሎ ስምዖን ጴጥሮስ ይቀውም ወይስሕን
፳፭ ጴጥሮስም ቁሞ እሳት ይሞቅ ነበር ፡፡
ወተስእልዎ እለ ይቀውሙ ወዓልት ወይቤልዎ አንተሂ እምአርዳኢሁ ለውእቱ ብእሲ አንተ ፡፡
አንተም ክርሉ ደቀ መዛሙርት ወገን ነህ አሉት፡፡
ወክህደ ወይቤ ኢኮንኩ ፡፡
አይደለሁም ብሎ ካደ ፡፡

፳፮ ወይቤሎ ፩ዱ እምአግብርቲሁ ለሊቀ ካህናት ዘእምአዝማዲሁ ለዝኩ ለዘመተሮ ጴጥሮስ እዝኖ እኮኑ አነ ርኢኩከ ውስተ ገነት ምስሌሁ ፡፡

፳፮ ጴጥሮስ ጆሮውን ከቆረጠው ከሊቀ ካህናቱ ባሪያ ወገን የሚሆን አንዱ ካታክልት ቦታ ክርሉ ጋራ አይቼህ አልነበረምን አለው የማልኮስን በቀል መለስኩ ብሎ ፡፡

፳፯ ወካዕበ ክህደ ጴጥሮስ ፡፡
፳፯ ለቀረበው ካዕበ እያለ ይሄዳል ጴጥሮስ ሁለተኛ ካደ ፡፡
ወበጊሁ ነቀወ ዶርሆ ሶቤሃ ፡፡
ያንጊዜ ዶሮ ጮኸ ፤ የክህደተ ጴጥሮስ መገናኛ እንደምን ነው በመጀመሪያ አንዳንድ ሴት በማለት አራቱ ሁሉ አንድ ናቸው ፡፡ በሁለተኛው ማቴዎስና ማርቆስ አንዳንድ ሴት ይላሉ ሉቃስ አንድ ወንድ ፤ ዮሐንስ ብዙ ወንዶች አለ ፣ በሦስተኛው ማቴዎስና ማርቆስ ብዙ ወንዶች ይላሉ ሉቃስና ዮሐንስ አንድ አሉ አይጣላም ቢሉ አይጣላም፥ በመጀመሪያ አራቱ ሁሉ አንዳንድ በማለት አንድ ናቸው ፡፡ በሁለተኛው ማቴዎስና ማርቆስ አንዲት ሴት ማለታቸው አንዲት ሴት ለብዙ ወንዶች ነግራለች ሉቃስ አንድ ወንድ ማለቱ ጠያቂውን ሲያይ ዮሐንስ ብዙ ወንዶች ማለቱ መጠየቅ የሁሉ ፈቃድ ከሆነ ብሎ፥በሦስተኛው ማቴዎስና ማርቆስ ብዙ ወንዶች ማለታቸው ፈቃድ የሁሉ ከሆነ ብለው ሉቃስና ዮሐንስ አንድ ወንድ ማለታቸው ጠያቂውን ሲያዩ ነው ፡፡
ዘከመ ቆመ ኢየሱስ ቅድመ ጲላጦስ ፡፡

፳፰ ወወሰድዎ ለእግዚእ ኢየሱስ እምኀበ ቀያፋ ኀበ ዓውድ ፡፡ ማቴ፥፳፯፥፪ ማር፥፲፭፥፩ ፡፡ ሉቃ፥ ፳፫፥፲፩ ግብ፥ ፲፥፳፰ ፡፡

፳፰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከቀያፋ ዘንድ ወደ ዐደባባይ ወሰዱት ፡፡
ወጎህ ውእቱ ፡፡
ማለዳ ነበር ፡፡
ወኢቦኡ አይሁድ ውስተ ዓውደ ምኵናን ፡፡
ካደባባይ አልተገናኙም ነበር
ከመ ኢይርኩሱ እምቅድመ ይብልዑ ፋሥሐ ፡፡
በግዓ ፋሲካውን ሳይበሉ ሥርዓት ማፍረስ እንዳይሆንባቸው ሐተታ ሲያመላልሱት አድረው ነግቶባቸዋል በቀትር በግዓ ፋሲካውን በልተው ወጥተው ሰቅለውታል ዛሬ የጥምቀትን ቍርባን ረፈደ ብለው እንዳይተውት ፡፡

፳፱ ወወፅአ ጲላጦስ አፍአ ኀቤሆሙ ፡፡
፳፱ ጲላጦስ እርሳቸው ወዳሉበት ወጣ ፡
ወይቤሎሙ ምንትኑ ጌጋዩ ለዝብእሲ በዘአምጻእክምዎ ኀቤየ
ወደኔ ባመጣችሁት ገንዘብ ወደኔ ያመጣችሁበት የዚህ ሰው በደሉ ምንድን ነው አላቸው ፡፡

፴ ወአውሥኡ አይሁድ ወይቤልዎ ሶበሰ ኢኮነ ገባሬ እኪት እምኢያግባእናሁ ኀቤከ ፡፡

፴ በደልስ ባልኖረበት ላንተ አባልፈንም ባል ስጠነው ነበር አሉት ፡፡

፴፩ ወይቤሎሙ ጲላጦስ ንሥእዎ አንትሙ ወበከመ ሕግክሙ ኰንንዎ ፡፡

፴፩ ጲላጦስም እናንተው ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት ግደሉት አላቸው ፡፡ አንተ ትኴንኖ ለእጉከ እንዲል ፡፡
ወይቤልዎ አይሁድ ለነሰ ኢይከውነነ ንቅትል ወኢመነሂ ፡፡
እኛስ ማንንም ማን ልንገድል አይቻለንም አሉት፡፡

፴፪ ከመ ይብጻሕ ቃሉ ለእግዚእ ኢየሱስ ዘይቤ እንዘ ይኤምሮሙ በአይ ሞት ሀለዎ ይሙት ማቴ፥ ፳ ፤ ፲፱ ፤

፴፪ በምን ሞት ይሞት ዘንድ አለው ቢሉ በምን ሞት ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያስረዳ ጌታ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ፤ እንዲሉ አደረጋቸው ፤ አንድም በምን ሞት ይሞት ዘንድ

አለው ቢሉ በመስቀል ተሰቅሎ ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያስረዳ እንዲህ እንዲሉ አደረጋቸው ። ሐተታ ስቅለት የሮም ነው አይሁድ በደንጊያ ነው የሚገሉ ።

፴፫ ወቦአ ካዕበ ጲላጦስ ውስተ ዓውድ ፤
፴፫ ዳግመኛ ጲላጦስ ካደባባይ ወጣ ።
ወጸውዖ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታን ጸራው ።
ወይቤሎ አንተኑ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።
የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን አለው ።

፴፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ
፴፬ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ ዘእምልብከኑ ትብል ዘንተ ።
ይህን የምትናገር ከራስህ አንቅተህ ነውን ።
ወሚመ ቦኑ ባእድ ዘነገረከ በእንቲአየ ።
ወይም የኔን ነገር የነገረህ ሌላ አለን አለው ።

፴፭ ወአውሥአ ጲላጦስ ።
፴፭ ጲላጦስም መለሰ ።
ወይቤሎ እንጋ አይሁዳዊኑ አነ ።
ከራሴማ አንቅቼ እናገር ዘንድ እኔ አይሁዳዊ ነኝን ።
አኮኑ ሕዝብከ ወሊቃነ ካህናት አግብኡከ ኀቤየ ።
ወገኖችህና የካህናት አለቆች ለኔ አሳልፈው ሰጥተውህ የለምን ።
ምንተኑ እግበረከ ።
ምን ላድርግህ ። አንድም ወገኖችህ ሊቃነ ካህናት ለኔ አሳልፈው ሰጥተውሀልና ።
ምንተኑ እገብረከ ።
ምን አደርግሃለሁ በደል የሌለብህን አለው ።

፴፮ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፴፮ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ መንግሥትየሰ ኢኮነት እምዝንቱ ዓለም
የኔ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም የተገኘች አይደለችም በዚህ ዓለም ብቻ አይደለችም ።
ሶበሰ ኮነት በዝንቱ ዓለም መንግሥትየ እምተበእሱ ሊተ ወዓልያንየ ከመ ኢያግብኡኒ አይሁድ ኀቤከ ።
መንግሥቴስ በዚህ ዓለም ብቻ ብትሆን ። አንድም ከዚህ ዓለም የተገኘች ብትሆን አይሁድ ላንተ አሳልፈው እንዳይሰጡኝ ብላቴኖቼ በተጣሉልኝ ነበር ።
ወይእዜሰ ባሕቱ ኢኮነት መንግሥትየ እምዝንቱ ዓለም ።
ነገር ግን መንግሥቴ በዚህ ዓለም ብቻ አይደለችም ከዚህ ዓለም የተገኘች አይደለችም ።

፴፯ ወይቤሎ ጲላጦስ እንከሰኬ ንጉሥ አንተ ።
፴፯ ጲላጦስም መንግሥትህ በዚህ ዓለም ብቻ አይደለችም ከዚህ ዓለም የተገኘች አይደለችም እንጂ መሆኑን ንጉሥ ነሃ አለው ።
ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታም መለሰ ፤
ወይቤሎ ለሊከ ትቤ ከመ ንጉሥ አነ ፤
እኔ ንጉሥ እንደሆንኩ አንተ ትናገራለህ አለው ። መሰወር ። አንድም በሦስቱ ዳኞች ልሳን ትጽፈዋለህ ።
ወአንሰ በአንተ ዝንቱ ተወለድኩ ወእንበይነ ዝንቱ መፃእኩ ውስተ ዓለም ከመ እኩን ሰማዕተ በጽድቅ ።
እኔ በእውነት እመሰክር ዘንድ ተወልጄ ስለዚህ ወደ ዓለም መጥቻለሁ ።
ወኵሉ ዘእምጽድቅ ውእቱ ይሰምዓኒ ቃልየ ።
ከጽድቅ የተገኘ የጽድቅ ወገን ሁሉ ነገሬን ይቀበለኛል ፤

፴፰ ወይቤሎ ጲላጦስ ምንትኑ ውእቱ ጽድቅ ።
፴፰ ጲላጦስም ጽድቁ ምንድ ነው አለው ፤
አንተም ንጉሥ ነኝ ትላለህ እኒያም ንጉሥ ነኝ አለ ብለው አምጥተውሃል እውነቱ ማናቸው ነው አለው ። አንድም ወኵሉ ዘእምጽድቅ ይሰምዓኒ ቃልየ ብሎት ነበርና ነገሩ ቢረቅበት ጽድቁ ምንድ ነው አለው ።
ወዘንተ ብሂሎ ወፅአ ካዕበ ኀበ አይሁድ ፤
ይህን ተናግሮ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጣ ።
ወይቤሎሙ አንሰ ኢረከብኩ ጌጋየ ላዕሌሁ ወኢአሐተኒ ።
እኔስ ጥቂት ለንኳን በደል አላገኘሁበትም አላቸው።

፴፱ ወባሕቱ ሀሎ ዘናለምድ ዘአሐዩ ለክሙ ፩ደ እምነ ሙቁሐን ለለፋሲካ ።

፴፱ ባመት አንዳንድ አስር የምንፈታበት ፤ አንድም አሐዩ ለክሙ ፡ እፈታላችሁ ዘንድ ያለመድነው ሥርዓት አለ ።
ትፈቅዱኑ አንከ ከመ እኀድግ ወአሕይዎ ለክሙ ለንጉሠ አይሁድ ።
የአይሁድ ንጉሥ ክርስቶስን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን አላቸው ።

፵ ወከልሑ ካዕበ ኵሎሙ ።
፵ መላው አሰምተው ተናገሩ ።
ወይቤሉ አኮ ዘንተ ዘተሐዩ ወተሐድግ ።
የምትፈታልን ይህን አይደለም ።
አላ በርባንሃ ።
በርባንን ነው እንጂ ።
ወበርባንሰ ሊቀ ፈያት ውእቱ ።
በርባን ግን የወንበዴ አለቃ ነው ።
እንዲህ ሲሆን በደል የሌለበትን ግደል በደል ያለበትን አትግደል አሉ ለማለት ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወእምዝ ነሥኦ ጲላጦስ ለእግዚእ ኢየሱስ ወቀሠፎ ።

፩ ዝ ሲናገረው የመጣው ነው ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ካልቀረሰ በምር ደስ ይበላቸው ብሎ ካደባባይ አውጥቶ ገረፈው ። አንድም ራርተው ይተውታል መስሎት ፡ አንድም መጠውኩ ዘባንየ ለመቅሠፍት ያለው ትንቢት ሊፈጸም ፡ አንድም ዲያብሎስ የአዳምን ዘባነ ልቡናውን እየገረፈ ገሃነም አውርዶት ነበርና ለርሱ ካሣ ሊሆን አንድም በጌታ የግፍ ድርብ ይደረግበታልና በሀገራቸው የሚሰቀል አይገረፍም እርሱን ግን ገርፈው ይሰቅሉታልና ።

፪ ወጸፈሩ አክሊለ ሦከ ።

፪ ጭፍሮች የሾህ አክሊል ጕንጉነው ።
ወአስተቀጸልዎ ላዕለ ርእሱ ።
ከራሱ ላይ ደፉለት እንነሥንህ ብለውታልና ፍና ተሣልቆ አንድም ወወደዩ ጌራ መድኃኒት ዲበ ርእሱ ያለው ትንቢት ሊፈጸም ፡ ድርሳነ መድኃኔ ዓለም ሽህ ጥቃቅን ሰብዓ ታላላቅ የብረት እሾህ ያለው ዘውድ ነው ይላል እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ነገር እንደዚህ ነው ይላል እንደዚያስ ከሆነ ኢትስብሩ ዓፅሞ ያለው በፈረሰ ነበር ።
ወአልበስዎ ልብሰ ሜላት ።
ነጭ ግምጃ አለበሱት ።
ማቴዎስ ቀይህ ይላል ከዚህ እንዲህ አለ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም መደቡ ነጭ ነው ኋላ ቀለም አግብተውታል ። አንድም በአንድ ወገን ሲያዩት ነጭ በአንድ ወገን ሲያዩት ቀይ ይሆናል እንደ ሌታ ቀን ግምጃ ። አንድም አልፎ አልፎ ቀለም ገብቷል እንደ ሱሲ መጠብር እንደ ቀሽ መሬ መታጠቂያ እንደ መረሻት ።

፫ ወይመጽኡ ኀቤሁ ወይቤልዎ በሐከ ንጉሠ አይሁድ ።

፫ ወደርሶ እየመጡ የአይሁድ ንጉሣቸው ቢሰኛህን ጸበኛህን አያውለው አያሳድረው አለት ሌላ ቢሰኛ ጸበኛ አለውን አያውለን አያሳድረን ሲያሰኛቸው ነው ።
ወይጸፍዕዎ ገጾ ።
ፊቱን በጥፊ መቱት ። ወመልታሕቴየ ለጽፍእት ። ያለው ትንቢት ሊፈጸም ። አንድም ዲያብሎስ የአዳምን ገጽ ልቡናውን እየጸፋ ገሃነም አውርዶት ነበርና ለርሱ ካሣ ሊሆን ።

፬ ወወፅአ ካዕበ ጲላጦስ አፍአ ወይቤሎሙ ናሁ አውፅአ ለክሙ ከመ ታእምሩ ከመ አልቦ ዘረከብኩ ላዕሌሁ ጌጋየ ወኢአሐተኒ ።

፬ ጲላጦስም ባደባባይ ወጥቶ ጥቂት ስንኳ ባንድ ወገን ስንኳ ያገኘሁበት በደል እንደሌለ ታውቁ ዘንድ እነሆ ወደ ዐደባባይ አስመጣላችኋለሁ አላቸው ።

፭ ወወፅአ እግዚእ ኢየሱስ አፍአ እንዘ ይትቄጸል አክሊለ ዘሦከ ።

፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የእሾህ አክሊል ደፍቶ ።
ወይለብስ ሜላት ።
ነጭ ሐር ለብሶ ወደ ዐደባባይ ወጣ ።
ወይቤሎሙ ጲላጦስ ነዋ ውእቱ ብእሲ ።
ያ ሰው እነሆ አላቸው ።

፮ ወሶበ ርእይዎ ሊቃነ ካህናት ወወዓልያኒሆሙ ለእግዚእ ኢየሱስ ከልሑ ።

፮ ብላቴኖቻቸውና ሊቃነ ካህናትም ጌታን ባዩት ጊዜ ጮሁ ።
ወይቤሉ ስቅሎ ። ስቀለው አሉት ።
ወይቤሎሙ ጲላጦስ ንሥእዎ አንትሙ ወለሊክሙ ስቅልዎ ጲላጦስም እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት ።
አንሰ ኢረከብኩ ላዕሌሁ ጌጋየ ።
እኔስ የሚሰቀልበት በደል ነውር አላገኘሁበትም አላቸው ።

፯ ወአውሥኡ አይሁድ ወይቤልዎ ንሕነሰ ሕግ ብነ ።

፯ አይሁድም መለሱለት አሉትም እኛስ ሥርዓት አለን ።
ወበከመ ሕግነ ርቱዕ ይሙት ።
እንደ ሥርዓታችን ሞት ይገባዋል ።
እስመ ወልደ እግዚአብሔር ረሰየ ርእሶ ።
የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሏልና አሉት ምን ይዘው እንዲህ አሉ ቢሉ በወልደ ሰሎሚት ልማድ አባቱ ግብጻዊ ነው እናቱ ዕብራዊት ናት የእናቱን ዘመዶች እናቱን ተከትሎ ወጣ ፡ በምድረ በዳ በገዳም ሳሉ ካንዱ ጋራ ተጣሉ በግብጽማ ሳላችሁ ያባቴ ባሮች አልነበራችሁምን አለው ። እስራኤል ይኸን ሰምተው ሁለት መቶ ካሥራ አምስት ዘመን የገዙን አልበቃቸው ብሎ እየተከተሉ እየመጡ ይሰድቡን ጀመር ብለው አዘኑ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር አመለከተ እስራኤል የኔ ባሮች ናቸው እስራኤልን ባሪያዬ ማለት አምላክ ነኝ ማለት አይደለምን ። ዘፀአት ይህን ሲናገር የሰማው አስቀድሞ ድንጊያ ይጣልበት ከዚህ በኋላ ግደሉት ብሎ ገድለውታል ።

፰ ወሰሚዖ ጲላጦስ ዘንተ ነገረ ፈርሀ ፈድፋደ ።
፰ ጲላጦስ ይህን ነገር ሰምቶ ፈጽሞ ፈራ።

ወቦአ ካዕበ ኀበ ዐውድ ።
ሁለተኛ ወደ ዐደባባይ ወጣ ።

፱ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ እምአይቴ አንተ።
፱ ትውልድህ ነገድህ ከወዴት ነህ አለው ።
ወኢተሰጥዎ እግዚእ ኢየሱስ ወኢምንተኒ ።
ጌታ ግን አልመለሰለትም ። እንዳልፈራ ለማጠየቅ እንዳለፈው ጨርስ ።

፲ ወይቤሎ ጲላጦስ ሊተኒ ኢትነብበኒሁ ።
፲ ጲላጦስም አለው ለኔም አትመልስልኝ ።
ኢተአምርሁ ከመ ብውህ ሊተ እቅትልከኒ ወብውህ ሊተ እሕዩከኒ ።
ብስቅልህስ ባድንህስ እንዲቻለኝ አታውቅምን አለው ።

፲፩ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፲፩ ጌታም መለሰ ።
ወይቤሎ ኢኮንከ ብውሐ ላዕሌየ እሙ ኢተውህበ ለከ እምሰማይ ።
ከሰማይ ካልተሰጠህ ማለት መለኮቴ በሥጋ ካልተሰጠህ ፡ አንድም ሥልጣኑ ካባቴ ካልተሰጠህ በኔ ሥሉጥ አይደለህም አንድም ምንም ምን ሥልጣን የለህም አለው ።
ወበእንተዝ ዘአግብአኒ ኀቤከ ዘየዓቢ ጌጋይ ላዕሌሁ ።
ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ በሰጠኝ በይሁዳ ጽኑ ፍዳ አለበት ።

፲፪ ወበእንተዝ ፈቀደ ጲላጦስ ከመ ይኅድጎ ወያሕይዎ ።

፲፪ ዘየአቢ ጌጋይ ላዕሌሁ ስላለው ጲላጦስ ሊያድነው ወደደ ።
ወከልሑ አይሁድ ወይቤሉ እመ አሕየውኮ ለዝንቱ ኢኮንከ አርኮ ለቄሣር ።
ይህን ካዳንከው የቄሣር ፈቃደኛው አይደለህም
ብለው አይሁድ አሰምተው ተናገሩ ።
እስመ ኵሉ ዘያነግሥ ርእሶ ዓላዊ ንጉሢ ውእቱ።
ራሱን ንጉሥ ነኝ የሚል ሁሉ ወሬኛ ንጉሥ ነውና።

፲፫ ወሰሚዖ ጲላጦስ ዘንተ ነገረ አውፅአ ለእግዚእ ኢየሱስ አፍአ ።

፲፫ የቄሣር ፈቃደኛው አይደለህም ያሉትን ጲላጦስ ሰምቶ ጌታን ወደ ውጭ አወጣው ።
ወነበረ ዲበ መንበር ውስተ መካን ዘስሙ ሊቶስጥሮስ በዕብራይስጥ ይብልዎ ገቦታ ።
በዕብራይስጥ ገቦታ የሚባል ንጽፍ ደንጊያ ባለበት ቦታ ወንበር አዘርግቶ ተቀመጠ ።

፲፬ ወዓርብ ፋሲካ ።
፲፬ ፋሲካቸው ዓርብ ነበረ ። አንድም ወዓርበ ይላል ፋሲካቸው አለፈ ተከተተ ።
ወውእቱ ጊዜ ቀትር ዘስሱ ሰዓት ።
ያውም ድልድል ቀትር ነበር ።
ወይቤሎሙ ጲላጦስ ለአይሁድ ነዋ ንጉሥክሙ ።
ጲላጦስ አይሁድን እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው ።

፲፭ ወከልሑ አይሁድ ወይቤሉ አእትቶ ወስቅሎ ።

፲፭ በሞት አርቀው ስቀለው ብለው አሰምተው ተናገሩ ።
ወይቤሎሙ ጲላጦስ ለንጉሥክሙኑ እስቅሎ ።
ጲላጦስም ንጉሣችሁን ልስቀለውን አላቸው ።
ወአውሥኡ ሊቃነ ካህናት ።
የካህናት አለቆችም መለሱ ።
ወይቤሉ አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሣር ።
ቄሣር ነው እንጂ ከቄሣር በቀር ንጉሥ የለንም አሉት ።

፲፮ ወእምዝ ወሀቦሙ ይስቅልዎ ።
፲፮ ከዚህም በኋላ ስቀሉት ብሎ ሰጣቸው ።
ወተመጠውዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ወአውፅዎ አፍአ።
ጌታን ተቀብለው ወደ ውጭ ይዘውት ወጡ ።

፲፯ ወወሰድዎ እንዘ ይጸውር መስቀሎ ውስተ መካን ዘስሙ ቀራንዮ ።

፲፯ መስቀሉን ተሸክሞ ቀራንዮ ከሚባል ቦታ ይዘውት ሄዱ ።
ወበዕብራይስጥ ይብልዎ ጎልጎታ ።
የተሰቀለበት ቦታ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ይባላል።

፲፰ ኀበ ሰቀልዎ ።
፲፰ ከዚያም ሰቀሉት ።
ወሰቀሉ ምስሌሁ ካልዓነ ክልኤተ ፈያተ ።
ከርሱም ጋራ ሁለት ወንበዴዎች ሰቀሉ ።
አሐደ እምለፌ ወአሐደ እምለፌ ።
አንዱን በቀኝ አንዱን በግራ
ወማእከሎሙ ኢየሱስሃ ።
ጌታንም በመካከላቸው ። አነገሥንህ ብለውታልና ፍና ተሳልቆ ቀኛዝማች ግራዝማች ቀኝ ቢትወደድ ግራ ቢትወደድ ሾምንልህ ለማለት ። አንድም ለማሳሳት በቀኝም በግራም የመጣው ይህ ምን ድነው ብሎ ይጠይቃል ወንበዴ ፡ ያሳ የመካከለኛው ስ ያስ ከኒህን ልዩ ነው ለማለት ። አንድም ተኈለቈ ምስለ ጊጉያን ያለው ትንቢት ሊፈጸም ይኸንም ከመ ይደምረኒ ምስለ ነፍሰ ጸድቃን ብሎ ተርጕሞታል ምሥጢሩ ግን እኛን ኃጥአንን በግራ ታቆመናለህ ሲያሰኛቸው ነው ።

፲፱ ወጸሐፈ ጲላጦስ መጽሐፈ ወአንበረ ዲበ መስቀሉ ።

፲፱ ጲላጦስም መጸሐፍ ጽፎ ከመስቀሉ ራስ በትርፉ ጠረቀው ።
ወይብል መጽሐፉ ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሦሙ ለአይሁድ ውእቱ ዝንቱ ።
ያብዳቤውም የናዝሬቱ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሣቸው ይህ ነው የሚል ነው ።

፳ ወብዙኃን እምነ አይሁድ አለ አንበብዋ ለይእቲ መጽሐፍ ።

፳ ያችንም ያብዳቤ ከአይሁድ ወገን የተመለከቷት ብዙ ናቸው ።
እስመ ቅሩብ ውእቱ መካን ለሀገር ኀበ ሰቀልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ጌታን የሰቀሉበት ቦታ ለከተማ እቅራቢያ ነበርና።
ወጽሒፈቱ ጽሑፍ ውእቱ በዕብራይስጥ ።
ጽሕፈቱም በዕብራይስጥ ልሳን ነበር ።
ወበጽርዕ ። በጽርዕም ።
ወበሮማይስጥ ።
በሮማይስጥም ። ዕብራዊ ቀያፋ ጽርእዊ ሄሮድስ ሮማዊ ጲላጦስ እሉና ። ምሥጢሩ ግን ወንጌል በሦስቱ ልሳን እንድትጻፍ ያጠይቃል ።

፳፩ ወይቤልዎ ሊቃነ ካህናት ለጲላጦስ ኢትጽሕፍ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።

፳፩ የካህናት አለቆች ጲላጦስን የአይሁድ ንጉሣቸው ነው ብለህ አትጻፍ አሉት ።
እላ ለሊሁ ይቤ ንጉሦሙ ለአይሁድ አነ ።
እሱ የአይሁድ ንጉሣቸው ነኝ አለ ብለህ ጻፍ እንጂ ።

፳፪ ወአውሥአ ጲላጦስ ።
፳፪ ጲላጦስም መለሰ ።
ወይቤሎሙ ዘጸሐፍኩ ጸሐፍኩ ።
የጻፍኩትን ጻፍኩ አላቸው ።
ዘፈኖኩ ፈኖኩ እንዲል ። በነገር ሲያኹት ውለው ነበርና ፈንታውን ያሻችዋል ።

፳፫ ወሐራስ ሶበ ሰቀልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ነሥኡ አልባሲሁ ወተካፈሉ ወረሰይዎ አርባዕተ ክፍለ ።

፳፫ ጭፍሮች ግን ጌታን ከሰቀሉት በኋላ ልብሱን ወስደው ካራት ተካፈሉት ።
ለለአሐዱ እምሐራ ።
ከጭፍራውም ለእንዱም ላንዱ ለእያንዳንዱ ።
ወክዳኖሂ እልታሃ ዘአልቦ ርፍአት ዘእምላእሉ እንመቱ ። ሥፍ የሌለበት ሥር ወጥ ቀሚሱን ግን ።

፳፬ ይቤሉ ኢንግምድ ወኢንስጥጥ ።
፳፬ እርስ በእርሳቸው እሉ እንቅደደው ።
እላ ንትፋሰስ ለዘረከቦ ይርከቦ ።
ለደረሰው ይደርሰው ዘንድ ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ ከመ ይብጻሕ ቃለ መጽሐፍ ዘይቤ ፡ ተካፈሉ አልባስየ ለርእሶሙ ።
ልብሴን ተካፈሉት ብሎ መጽሐፍ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ። ረሰይዎ አርባዕተ ክፍለ ወተዓፀው ዲበ አራዝየ ። በልብሴ ዕፃ ተጣጣሉበት ብሎ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ። ወተበሀሉ ኢንግምድ ላለው ። ኵፌቱን መጠምጠሚያውን መጐናጸፊያውን ቀሚሱን ልብ አልባውን አርገው ተካፍለዋል ። ቀሚሱን ግን ልብስ ምንንት ብለው ንቀው ትተዋታል ። ንቀዋትስ አይደለም አከብረዋት ነው እንጂ። ሰብእ ስጋል ያመጡለት ሲያድግ የምታድግ አለ እንተ ደም ይውኃዛ የተፈወሱባት ገባሬተ ተእምራት ናት እይንቋትም ። ኩፌቱን መጠምጠሚያውን እንድ ወገን አድርገው ሦስት ዕፃ ይጥላሉ አራተኛ ዕፃውን ይዞ ያቆያል እንደገና አራቱ በርሷ ዕፃ ይጥላሉ ለደረሰው የደረሰች እንደሆን ያን ላልደረሰው ሰጥቶ እርሷን ይውሰዳል ። ላልደረሰው የደረሰች እንደሆን የተመቸ ። ለጊዜው እርሱ ሁለት ልብስ አታኑሩ ይላል የእንድ ባሕታዊ ልብስ ላራት ቤት ጭፍራ በቃ ለማለት ። ምሥጢሩ ግን ልብስ የወንጌል ምሳሌ ፡ አራት ዕፃ መጣጣላቸው ወንጌል አራት ወገን ሁና ለመጻፏ አለመቅደዳቸው በምሥጢር እንድ የመሆንዋ ። አንድም መለኮቱን ከትስብእቱ ትስብእቱን ከመለኮቱ ሳንለይ አንመን ሲያሰኛቸው ነው ።
ወከመዝ ገብሩ ሐራ ።
ጭፍሮች እንዲህ አደረጉ ።

፳፭ ወይቀውማ ኀበ መስቀሉ ለእግዚእ ኢየሱስ እሙ ወእኅታ ለእሙ ።

፳፭ እመቤታችን ሰሎሚ ።
ወማርያም እንተ ቀለዮጳ ።
ማርያም ባውፍልያ እንድም እኅታ ለእሙ ማርያም እንተ ቀለዮጳ ። ሐና ከሞተች በኋላ የቀለዮጳን ሚስት እግብቶ ወልዷታል ።
ወማርያም መግደላዊት ።
ማርያም መግደላዊት ከእግረ መስቀሉ እጠገብ ቁመው ነበር ።

፳፮ ወሶበ ርእዮሙ እግዚእ ኢየሱስ ለእሙ ወለረድኡ ዘያፈቅር ይቀውሙ ።

፳፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወደውን ደቀ መዝሙሩንና እመቤታችንን ከእግረ መስቀል

ቁመው ባያቸው ጊዜ ።
ወይቤላ ለእሙ ኦ ብእሲቶ ነዋ ወልድኪ ።
አንች ሆይ ልጅሽ ይርዳሽ ያጥናናሽ አላት ።
ውሉድኪ ሲል ነው ፤ በዮሐንስ እኛን ለርዕ መስጠቱ ነውና ።

፳፯ ወይቤሎ ለውእቱኒ ረድእ ነያ እምከ ።

፳፯ ደቀ መዝሙሩን እነሆ እናትህ ታጽናህ አለው እምከሙ ሲል ነው በዮሐንስ እርስዋን ለኛ መስጠቱ ነውና ።
ወእምይእቲ ሰዓት ነሥእ ውእቱ ረድእ ወአእተዋ ቤቶ።
ከዚያም ቀን በኋላ ዮሐንስ ወደቤቱ ይዝዋት ሄደ ።
ከዮሐንስ ቤት ዓሥራአምስት ዓመት ተቀመጠች ።

፳፰ ወእምዝ ሶበ ርእየ እግዚእ ኢየሱስ ከመ ተፈጸመ ኵሉ ።

፳፰ ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ትንቢት እንደ ተፈጸመ ባየ ጊዜ ።
ከመ ይብጻሕ ቃለ መጽሐፍ ይቤ ጸማዕኩ ።
መጽሐፍ ወወደዩ ሐሞተ ውስተ መብልዕየ ያለው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ጸማዕኩ አለ ።

፳፱ ወቦቱ ህየ ግምዔ ዘምሉእ ብሒዓ ።
መጣጣ የተመላ ማሰሮ ከዚያ አለ ።
ወመልኡ ሰፍነገ ወቈጽለ ሁስጹ ወመልኡ ውስቴቱ እምውእቱ ብሒዕ ።
እንዳይነ በጐ ያለ ባዘቶ ውኃ የሚያነሣ ቤታቸውን የሚጠርጉበት ነው ያን ከመጣጣው ነከረው ።
ወአሠሩ በቈጽለ ሁስጹ ዲበ ሕለት ወአስተርከቡ ውስተ አፉሁ ወአፀሩ ።
በስሚዛ ዘንግ አስረው ካፉ ጠመቁለት ።
ወሰረቦ ብሒዓ ኢየሱስ ይቤ ናሁ ተፈጸመ ኵሉ ዘጽሑፍ። ኢየሱስም መጻጻውን በቀመሰ ጊዜ የተጻፈው ሁሉ ደረሰ ተፈጸመ አለ ። በሀገራቸው አራት ነገር ያመጸሉ የስንዴ ቅጥራን የበለስ ቅጥራን አዞ ከል ዝፍተ ወይን ። ሐሞቱን ግን እነሱ አልጨመሩትም ሊሽጠው ገበያ ይዞት ወጥቶ ረከሶበት ሊጥሰው ወዶ ቈሞ ሳለ ተቀዶ ገብቷል ።
ወአጽነነ ርእሶ ።
ራሱን ዘለፍ አደረገ ።
ወመጠወ ነፍሶ ወወፅአት መንፈሱ ።
ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በእደ እግዚአ ብሔር ለየ ።
ወአይሁድሰ ። አይሁድ ግን ።
እስመ ዓርብ ውእቱ ።
መሽቷልና ።
ይቤሉ አላንቱ ሥጋት ኢይቢታ ዲበ መላቅሊሆን።
እኚህ ሰዎች እንደተሰቀሉ አይደሩ አሉ ።
በእንተ ሰንበት ።
ስለ ክብረ ሰንበት ።
እስመ ዓባይ ዕለታ ለይእቲ ሰንበት ።
ዕለቲቱ ክብርት ናትና ።
ወሰአልዎ ለጲላጦስ በኀቡእ ከመ ያውርድዎሙ ሰቢሮሙ ቀኖፂሆሙ ።
ጭን ጭናቸውን ሰብረው ያወርዷቸው ዘንድ በስውር ጲላጦስን ለመኑት ።

፴፪ ወመጽኡ ሐራ ወሰበሩ ቀኖፆ ለቀዳማዊ ።

፴፪ ጭፍሮችም መጥተው የፈያታይ ዘየማንን ጭኑን ሰበሩት ፈቱን ወደርሱ መልሶ ተሰቅሎ ነበርና ቀዳማዊ አለ ።
ወለካልዑኒ ዘተሰቅለ ምስሌሁ ።
ከርሱ ጋራ የተሰቀለውን ፈያታይ ዘፀጋምን ።

፴፫ ወሶበ ሖሩ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወርእይዎ ወረከብዎ ከመ ሠለጠ መዊተ ።

፴፫ ጭፍሮች ከጌታችን ዘንድ ሄደው ፈጽሞ ሙቶ አገኙት ወኢሰበሩ ቀኖፆ ።
ጭኑን አልሰበሩትም ።

፴፬ አላ ፩ዱ እምሐራ ረገዞ ገቦሁ ዘየማን በኩናት ።

፴፬ ከጭፍሮች አንዱ አለን ሞተ ብሎ ቀኝ ጐኑን በጦር ወጋው እንጂ ።
ወሶቤሃ ወፅአ እምኔሁ ደም ወማይ ።
ያንጊዜ ጥሩ ውኃ ትኩስ ደም ፈሰሰ ፤ ሐተታ እንደ ለ ሁኖ ከላይ አንድ ከታች እየራሱ ከላይ አንድ መሆኑ የተዋሕዶ ከታች እየራሱ መሆኑ የተዓቅቦ።

፴፭ ወዘርእየ ስምዓ ኮነ ።

፴፭ ያየ ሐራዊ ያየ ወንጌላዊ መሰከረ ።
ወጽድቅ ውእቱ ስምዑ ።
ሀውቆ ያስተምራል ብሎ ምስክርነቱ እውነት ነው ።
ወአእመረ ውእቱ ከመ ጽድቀ ይነግር ።
እውነት እንዲያስተምር አወቀ ።
ከመ አንትሙሂ ትእመኑ ።
እናንተም ታምኑ ዘንድ ።

፴፮ ወዝንቱ ነገር ከመ ይብጻሕ ቃለ መጽሐፍ ዘይቤ ዓፅሞ ኢትስብሩ እምኔሁ ።

፴፮ ይህ ነገር የሆነ መጽሐፍ ዓፅሙን አትስበሩ ብሎ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ።

፴፯ ወካዕበ ይብል ካልዕኒ መጽሐፍ ሀለዎሙ ይርአይዎ ለዘወግዕዎ ።

፴፯ ዳግመኛም ሌላው መጽሐፍ እጁን እግሩን በቀኖት የቸነከሩትን ጐኑን በጦር ወግተው ያዩት ዘንድ አላቸው ብሎ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ፤ ፩ዱ እምሐራ ረገዞ ገቦሁ ላለው ። አንድም

እጁን እግሩን በቀኖት የቸነከሩት ጐኑን በጦር የወጉት በተአምራት ያዩት ዘንድ አሳቸው ብሎ መጽሐፍ የተናገረው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ወፅአ እምኔሁ ደም ወማይ ። የወጋው አንድ ሐራዊ አይደለምን ቢሉ ሽ በመከረ አንድ ወረወረ እንዲሉ ፈቃድ የሁሉ ከሆነ ብሎ አንድም መጽሐፍ ስም ካልጠራ ማብዛት ልማድ ነውና ካህናት ኀሉፋነ ፍኖት ከበቱ ፍኖተ እግዚእሙ እንዲል ። አንድም በቀኖት እጁን እግሩን የወጉትን ደርቦ ቈጥሮ ወማዕም አለ ።

፴፰ ወእምድኅረ ዝንቱ ሰአሎ ለጲላጦስ ዮሴፍ ዘአርማትያስ ።

፴፰ ከዚህ በኋላ የአርማትያስ ሰው የሚሆን ዮሴፍ ጲላጦስን ለመነው ።
እስመ ዝንቱ ረድዑ ውእቱ ለእግዚእ ኢየሱስ።
የጌታ ደቀ መዝሙሩ ነበርና ።
ወኮነ የኀብእ ለዝንቱ በእንተ ፍርኃቶሙ ለአይሁድ ።
አይሁድን ስለ ፈራ ደቀ መዝሙርነቱን ይሰውር ነበር ።
ከመ ይንሣእ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
ሰአለ ከመ ይንሣእ ። እንበሳ የገደለው ንጉሥ ያስቀሰው ይታፈራልና ላውርድ ብሎ ለመነ ።
ወአብሖ ጲላጦስ ወሖረ ውእቱኒ ወነሥአ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
አውርድ አለው እሱም ሄዶ የጌታን ሥጋ አወረደ ።

፴፱ ወመጽአ ኒቆዲሞስኒ ዘሖረ ኀቤሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ቀዲሙ ሌሊተ ።

፴፱ አስቀድሞ በሌሊት ወደጌታ የሄደ ኒቆዲሞስም መጣ ።
ወአምጽአ በዘቦቱ ይቀብርዎ ሕውስ ከርቤ ወዐልወ ።
ገንዘው የሚቀብሩበትን የደቀቀ የጣፈጠ ሽቱአመጣ።
ምእተ ልጥረ ፤
መቶ ምዝን መቶ ግግር ዋግራ ሽቱ የሬት ሽቱ።

፵ ወነሥኡ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
፵ የጌታን ሥጋ አውርደው ።
ወገነዝዎ በመዋጥሀ ከታን ዘሰንዱናት ምስለ አፈው በከመ ሕገ አይሁድ ሶበ ይገንዙ ወይቀብሩ ።
አይሁድ ገንዘው በሚቀብሩበት ጊዜ እንደሚያደርጉት ሥርዓት ሽቱ ቀብተው በድርብ በፍታ ገነዙት ።

፵፩ ወቦ ሀየ ገነት ውስተ ውእቱ መካን ኀበ ሰቀልዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፵፩ ጌታ የተሰቀለበት ቦታ የተክል ቦታ ነበር ።

ወውስተ ውእቱ ገነት ዝሀር ሐዲስ ዘአልቦ ዘተቀብረ ውስቴቱ ።
ከዚያም ቦታ ሰው ያልተቀበረበት አዲስ ቦታ ነበር።

፵፪ ወሀየ ቀበርዎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
፵፪ ጌታን ከዚያ ቀበሩት ። እንግዳ ሥርዓት እሠራላችኋለሁ ለማለት ። አንድም እንደ ኤልሳዕ ገባሬ ተአምራት ነቢይ ከተቀበረበት ቢቀበር ያ አሥነሣው እንዳይሉ ።
እስመ ተፍጻሜተ ዓርቦሙ ውእቱ ለአይሁድ ።
የአይሁድ መከተቻቸው ነበርና ።
ወቅሩብ ውእቱ መቃብር ኀበ ሰቀልዎ ።
መቃብሩ ለተሰቀለበት ቦታ አቅራቢያው ነበር ።
ያሥራሁለቱ ነገደእስራኤል ቦታ በየርስታቸው ነው ገሊላ ከእናቱ ርስት ወስደው እንዳይቀብሩት መሹቶባቸው ከዚያው ቀብረውታል ።

ዘከመ ሖሩ ማርያም መግደላዊት ወጴጥሮስ ወዮሐንስ ውስተ መቃብር ።

ምዕራፍ ፳ ።

፩ ወበእሑድ ሰንበት መጽአት ማርያም መግደላዊት ኀበ መቃብር ። ማቴ፡፳፰፡፩ ማር፡ ፲፮፡፩ ሉቃ፡ ፳፬፡፩ ።

፩ ባንድ ሰንበት አንድም መጀመሪያው ሰንበት ፡ እሑድ ሰንበት በተባለበት ቀን ማርያም መግደላዊት ማለዳ ገሥግሣ ወደ መቃብር መጣች።
እንዘ ዓዲሁ ጽልመት ።

ገና ጨለማው ሳይለቅ ገና ጨለማ ሳለ ።
ወረከበት እብነ እቱተ እምእፈ መቃብር ።
ደንጊያውን ከመቃብሩ ተነሥቶ አገኘችው ።

፪ ወሮጸት ወበጽሐት ኀበ ስምዖን ጴጥሮስ ወኀበ ዝኩ ካልዕ ረድእ ።

፪ ከባለሟሉ ከዮሐንስና ከጴጥሮስ ዘንድ ፈጥና ሄደች ።
ወትቤሎሙ ነሥእዎ ለእግዚእየ እምውስተ መቃብር
ጌታዬን ከመቃብር አውጥተው ወስደውታል ።
ወኢየአምር ኀበ ወሰድዎ ።
ከወሰዱበት ግን አላውቅም ።

፫ ወወፅኡ ኀቡረ ስምዖን ጴጥሮስ ወዝኩ ካልዕ ረድእ ወሖሩ ኀበ መቃብር ።

፫ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወጥተው ወደ መቃብር ሄዱ።

፬ ወእንዘ ይረውጹ ክልኤሆሙ ኀቡረ ።
፬ ሁለቱ ፈጥነው አንድ ሁነው ሲሄዱ በዶሮ ለጴጥሮስ ዝኩ ካልዕ ረድእ በጺሐ ኀበ መቃብር ።

ዮሐንስ ጴጥሮስን ቀድሞት ወደ መቃብር ሄደ ሕፃን ነውና በፍቅሩ ይናደዳልና ።

፭ ወሶበ ሐወጸ ርእየ መዋጥሐ ንቡረ ።
፭ ዘልቆ በተመለከተ ጊዜ መጐናፀፊያውን አገኘ ።

ወኢቦአ ባሕቱ ።
ነገር ግን አልገባም ። ሕፃን ነውና ቢፈራ ። አንድም ስለ ክብረ ጴጥሮስ ። ከኤጲስቆጶስ አስቀድሞ ከመቅደስ እንዳይገባ

፮ ወተለዎ ስምዖን ጴጥሮስ ወበጽሐ ።
፮ ስምዖን ጴጥሮስ ተከትሎት ደረሰ ። አረጋዊ ነውና በኀዘን ተቀጥቅጧልና ።
ወቦአ ውስተ መቃብር ።
ወደ መቃብር ገባ ። ኤጲስቆጶስ ከቄስ አስቀድሞ መቅደስ እንዲገባ ።
ወረከበ መዋጥሐ ንቡረ ውስተ አሐዱ ገጽ ።
መጐናፀፊያውን ባንድ ወገን አገኘ ።

፯ ወሰበነኒ ዘዲበ ርእሱ እንተ ባሕቲቱ ጥብሉለ ።

፯ ሻሹን እንደተጠመጠመ ለብቻው ።
ወአኮ ምስለ መዋጥሀ ።
ከመጐናፀፊያው ጋራ ሳይቃወስ ።

፰ ወእምዝ ቦአ ዝኩኒ ካልዕ ረድእ ዘበደሮ በጺሐ ኀበ መቃብር ።

፰ ከዚህ በኋላ ቀድሞ ከመቃብር የደረሰ ዮሐንስም ገባ ቄስ ኤጲስቆጶስን ተከትሎ መቅደስ እንዲገባ ።
ወርእዩ ወእምኑ
ትንሣኤውን አይተው አመኑ ።

፱ እስመ ዓዲሁ ኢየእምሩ ዘውስተ መጻሕፍት ዘከመ ሀለዎ ይትንሣእ እምነ ምውታን

፱ ከሙታን ተለይቶ ይነሣ ዘንድ እንዳለው መጻሕፍት የተናገሩትን ገና አላወቁም ነበርና ።

፲ ወእምዝ ሖሩ ፪ኤሆሙ አርዳኢሁ ።
፲ ከዚህ በኋላ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ሄዱ።
ወአተው ቤቶሙ ።
ከቤታቸው ገቡ ።
ዘከመ አስተርአያ ኢየሱስ ለማርያም መግደላዊት።

፲፩ ወማርያምሰ ቆመት ኀበ መቃብር አፍአ ወትበኪ ። ማቴ፡ ፳፰፡፩ ማር. ፲፮፡፩ ሉቃ ፳፬፡፩

፲፩ ማርያም ግን ከመቃብር አጠገብ ሁና ታለቅስ ነበር ።
ወእንዘ ትበኪ ሐወጸት ውስተ መቃብር ።
እያለቀሰች ወደ መቃብር በተመለከተ ጊዜ።

፲፪ ወርእየት ክልኤተ መላእክተ በጸዓድው አልባስ ።

፲፪ ሁለት መላእክት ብሩህ ብሩህ ልብስ ለብሰው አየች ።
ወይነብሩ አሐዱ ትርዓሰ ወአሐዱ ትርጋፀ ኀበ ነበረ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
የጌታችን ሥጋ ካለበት ቦታ አንዱ በራስጌ አንዱ በግርጌ ተቀምጠው ።

፲፫ ወይቤልዋ እሙንቱ መላእክት ምንት ያበክየኪ አ ብእሲቶ

፲፫ እኒያ መላእክት አንች ሆይ ምን ያስለቅስሻል አሏት ።
ወመነ ተኃሥሢ ።
ማን ትሻለሽ ።
ወትቤሎሙ እስመ ነሥእዎ ለእግዚእየ እምውስተ መቃብር ።
ጌታዬን ከመቃብር ወስደውታል ።
ወኢየአምር ኀበ ወሰድዎ ።
ከወሰዱበት ግን አላውቅም አለቻቸው ።

፲፬ ወዘንተ ብሂላ ተመይጠት ድኅሬሃ ።
፲፬ ይህን ተናግራ ወደኋላ ተመለሰች ያዘነተኛ ዓይኑ ቢካና ነውና አንድም መላእክት ከወደፊቷ ሲሰግዱ አይታለች ከወደኋላዋ ጥላውን ጥሎባታል መለስ ብትል ቁሞ አይታዋለች ።
ወኢያእመረት ከመ እግዚእ ኢየሱስ ውእቱ ።
ጌታ እንደሆነ አላውቀችም ።

፲፭ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ብእሲቶ ምንት ያበክየኪ ።

፲፭ አንች ሆይ ምን ያስለቅስሻል ።
ወመነ ተኃሥሢ ።
ማንንስ ትሻለሽ አላት ።
ወመሰላ ላቲስ ዓቃቤ ገነት ውእቱ ።
እርሷም አታክልት ጠባቂ መሰሏት ነበር ።
ወትቤሎ እግዚእየ እመኒ አንተ ነሣእኮ ንግረኒ ኀበ ወሰድኮ ።
ጌታዬ አንተ ወስደኸው እንደሆነ ንገረኝ አለችው ።
ከመ አሑር አነ ወእንሥኦ ኀቤየ ከመ ዕቅብእ ዕፍረተ ወደኔ አምጥቼ ሽቱ ዕቀባው ዘንድ ።

፲፮ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ለማርያም ።
፲፮ ጌታ ማርያም አላት ።
ወተመይጠት ወትቤሎ በነገረ ዕብራይስጥ ረቡኒ ።
ተመልሳ በዕብራይስጥ ቋንቋ ረቡኒ አለች ።
ዘበትርጓሜሁ ሊቅ ብሂል ውእቱ ።
መምህር ሆይ ማለት ነው ።

፲፯ ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ኢትልክፍኒ እስመ ዓዲ ኢዐረጉ ኀበ አቡየ ።

፲፯ የተግሣጽ አነጋገር ወዳባቴ አልወጣሁም ማለት ገና አላመንሽብኝምና አትንኪኝ አላት ። አንድም የመስናበቻው ጊዜ የደረስ መስሏት ቀር ባለች የማርገበት ጊዜ ገና ነውና አትንኪኝ አላት፥ ክህናት ልብስ ተክህኖ ለብሰው ሳሉ ሊነኳቸው እንዳይገባ ለማጠየቅ ።
ወሑሪ ባሕቱ ኀበ አኃውየ ወበሊዮሙ እዓርግ ኀበ አቡየ ወአቡከሙ ኀበ አምላኪየ ወአምላክክሙ ። ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ ወዳባቴ ወዳባታችሁ ወደ ፈጣሪየ ወደፈጣሪያችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው እንጂ አላት አቡየ ብሎ የሱን ልደት ተናገረአቡየ ያለው የርሱ የባሕርይ ነው አቡክሙ ያለው የኛ የጸጋ ነው አምላኪየ አለ በሥጋ ይፈጥረዋል ፥ አምላክክሙ አለ በጥንተ ተፈጥሮ በሐዲስ ተፈጥሮ ይፈጥረናልና።

፲፰ ወሖረት ማርያም መግደላዊት ወአብሠረ ቶሙ ለአርዳኢሁ ።

፲፰ ማርያም መግደላዊትም ሄዳ ለደቀ መዛ ሙርቶቹ ነገረቻቸው ።
ወትቤሎሙ ርኢክዎ ለእግዚእነ ወነገረኒ ዘንተ ። ጌታችንን አየሁት ይህንም ነገረኝ ብላ ።
ዜነወት ዘንተ ዘከመ ይቤላ ።
ተነሣ ብለሽ ንገሪ እንዳላት ተነሣ ብላ ነገረቻቸው፥ ማቴዎስ ብዙ ሴቶት በአፍአ አንድ መልአክ አዩ ይላል ፡ ማርቆስ ብዙ ሴቶች በውስጥ አንድ መልአክ አዩ ይላል ። ሉቃስ በአፍኦ በውስጥ ሳይል ብዙ ሴቶች ሁለት መላእክት አዩ ይላል ። ዮሐንስ አንዲት ሴት በውስጥ ሁለት መላእክት አየች አለ ። እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አይጣላም ማታ ጀምረው ሲመላለሱ አድረዋል እንደመጡ አይተዋል ። ሁለተኛ እንደ ማቴዎስ ባንድ ወገን የሄዱ ብዙ ሴቶች በአፍአ አንድ መልአክ አይተው ሄዱ ። እንደ ማርቆስ ባንድ ወገን የሄዱ ብዙ ሴቶች በውስጥ አንድ መልአክ አይተው ሄዱ ። ሉቃስ በአፍአ በውስጥ አይልም ባንድ ወገን የመጡ ሴቶች ሁለት መላእክት አይተው ሄዱ ፡ ዮሐንስ አንዲት ሴት በውስጥ ሁለት መላእክት አየች ማለቱ ለመንገር ከበቃች ብሎ ። አንድም እንደ ዮሐንስ ወሮጸት ወበጽሐት ኀበ ስምዖን ጴጥሮስ ወኀበ ዝኩ ካልዕ ረድእ ወትቤሎሙ ነሥእዎ ለእግዚእየ ብላ ተናገረች እንደ ማቴዎስ ባንድ ወገን የመጡ ብዙ ሴቶች በአፍአ አንድ መልአክ አይተው ሲሄዱ ጌታን ከመንገድ አገኙት ። ወቀርባ ወአኀዛ እገሪሁ ወሰገዳ ሎቱ ይላል ። እጅ ነሡት ። ሐሩ ንግርዎሙ ለአኃውየ አላቸው እንደ ሉቃስ ኢአምንዎን ወአክሀድዎን ወመ ሰሎሙ ከመ ዝንጋኤ ይላል አእምሮ የማጣት መስ ሏቸው እንደ ማርቆስ ባንድ ወገን የመጡ ብዙ ሴቶች በውስጥ አንድ አይተው ሲሄዱ በፍቅሩ ትናደዳለችና ከመቃብር በአፍአ እያስቀሰች ቀረች ። በውስጥ ሁለት መላእክት አይታለች አንዱን በራሱጌ አንዱን በግርጌ ማቴዎስ ሠርከ ሰንበት ለጸቢሐ እሑድ ማርቆስ ወእንግሃ ሉቃስ ኢሌ ሲያ ገይሠ ዮሐንስ እንዘ ዓዲሁ ጽልመት ይላል ማታ ጀምረው እስኪነጋ ድረስ ሲመላለሱ አድረዋል ። አንድም ማቴዎስ ሠርከ ሰንበት ሉቃስ ኢሌሲያ ዮሐንስ ዓዲሁ ጽልመት ይላል ፥ ለመዓልት ሠርክ እንዳለው ለሌሊትም ሠርክ አለውና ፥ ማቴዎስ ለጸቢሐ እሑድ ማርቆስ ወሶበ ሠረቀ ፀሐይ ሉቃስ ገይሠ ዮሐንስ በጽባሕ ያለው አንድ ነው ሲነጋ ማለት ነው ።

ዘከመ አስተርአዮሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት ።

፲፱ ወመስዮ ውእቱ ዕለት ዘውእቱ እሑድ ሰንበት እንዘ ዕፁው ኆኅት ኀበ ህለዉ አርዳኢሁ ጉቡአነ በእንተ ፍርሃቶሙ ለአይሁድ ማቴ.፳፰ ፥ ፩ ፤ ማር. ፲፮ ፡ ፩ ፤ ሉቃ. ፳፬ ፡ ፩ ።

፲፱ ያውም ሰንበት የተባለ እሑድ ነው ሲመሽ ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን ስለፈሩ በዝግ ቤት ተሰብስበው ሳሉ ።
መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ወቆመ ማእከሎሙ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ በዝግ ቤት ገብቶ በመካከላቸው ቆመ ።
ወይቤሎሙ ሰላም ለክሙ ።
እንዴት ሰነበታችሁ እስታረቅኋችሁ አላቸው ።

፳ ወዘንተ ብሂሎ አርአዮሙ እደዊሁ ወእገሪሁ ወገቦሁ ።

፳ በዚህ ያልተያየዘ በሉቃስ የተያያዘ ፈርሁ ወደንገፁ ወመሰሎሙ ከመ ዘመንፈስ ይሬእዩ ምትሒት ያዩ መስሏቸው እንዳዩ አድርገው ደነገፁ ፈሩምንት ያደነግፁክሙ ወስምንት ሐሊና እኩይ የዓርግ ውስተ ልብክሙ ፡ ርእዩ እደውየ ወእገርየ ከመ አነ ውእቱ ወገሥሡኒ ወአእምሩ እስመ ለመንፈስሰ ሥጋ ወዓፅም አልቦቱ ዘከመ ትሬእዩ ብየ ። በኔ እንደምታዩት ለምትሐት ሥጋ ዓፅም የለውም አላቸው ፡ ይህን ተናግሮ በቀኖት የተወጋውን እጁን እግሩን በጦር የተወጋውን ጐኑን አሳያቸው ።
ወተፈሥሑ አርዳኢሁ ሶበ ርእይዎ ለእግዚእነ ። ደቀ መዛሙርቱ ጌታን ባዩት ጊዜ ደስ አላቸው ።

፳፩ ወካዕበ ይቤሎሙ እግዚእነ ኢየሱስ ሰላም ለክሙ ።

፳፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፪ኛ እንዴት ሰነበታችሁ መስቀል ቀረባችሁ ፤

በከመ ፈነወኒ አብ ከማሁ አነኒ እፌንወክሙ ።
አባቴ እኔን ሙት ተሰቀል እንዳለኝ እኔም ሙቱ ተሰቀሉ እላለሁ ።

፳፪ ወሀንተ ብሂሎ ነፍሐ ላእሌሆሙ ወይቤሎሙ ንሥኡ መንፈሰ ቅዱሰ ።

፳፪ ይህን ተናግሮ ንሥኡ መንፈሰ ቅዱስ ብሎ በንፍሐት ቅስናን ሾማቸው ። ቅስናስ በሌላ ጊዜ ነው ብሎ ንሥኡ መንፈሰ ቅዱሰ ብሎ ልጅነት ሰጣቸው ።

፳፫ ለእለ ኃደግሙ ለሰብእ ኃጢአት ይትኃደግ ሎሙ ። ማቴ ፲፰፡፲፰ ፡

፳፫ ክልጅነት ቀጥሎ ቅስናን ሾማቸው ኃጢአት ላስተሰረያችሁላቸው ኃጢአት ይሰረይላቸው።
ወለእለሰ ኢኃደግሙ ኢይትኃደግ ሎሙ ።
ላላስተሰረያችሁላቸው ግን አይሰረይላቸው አላቸው

ዘከመ ተጠየቀ ቶማስ ።

፳፬ ወቶማስ ፩ዱ እም ፲ ወ፩ዱ አርዳኢሁ ዘይብልዎ ዲዲሞስ ኢሀሎ ምስሌሆሙ ሶበ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ኀቤሆሙ ፡

፳፬ ዲዲሞስ የተባለ ዐሥራ አንደኛው ቶማስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዝግ ቤት ገብቶ ሰላም ለክሙ ባላቸው ጊዜ ክርሳቸው ጋር አልነበረም ።

፳፭ ወይቤልዎ ካልዓኒሁ አርዳእ ርኢናሁ ለእግዚእነ ።

፳፭ ወንድሞቹ ሐዋርያት ጌታን እየነው አሉት ።
ወይቤሎሙ እመ ኢርኢኩ እደዊሁ ወእገሪሁ ኀበ ቀነውዎ ።
በቀኖት ። የተቸነከረውን እጁን እግሩን ካለየሁ ።
ወእመ ኢወደይኩ አፅባእትየ ውስተ ቅንዋቲሁ ወእመ ኢያባእኩ እዴየ ውስተ ገቦሁ ወኢገሠሥኩ ኢየአምን ።
በቀኖት የተቸነከረውን እጁን እግሩን በጦር የተወጋውን ጐኑን ካልዳሰስኩ አላምንም አላቸው ጥንተ ሰዱቃዊ ነውና እንድም ይገባዋል እኒያ እየን ብለው ሲያስተምሩ እርሱ ሰማሁ ብሎ የሚያስተምርን ነው ።

፳፮ ወእምድኅረ ሰሙን መዋዕል እንዘ ሀሰዉ ካዕበ አርዳኢሁ ውስጠ ።

፳፮ ዳግመኛ ከስምንት ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በዝግ ቤት ሳሉ ።
ወቶማስኒ ሀሎ ምስሌሆሙ ።
ቶማስም ክርሳቸው ጋራ ሳለ ።
ወእንዘ ዕፅው ኆኅት ።
ደጁ ተዘግቶ ።
መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ወቆመ ማእከሎሙ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ በመካከላቸው ቆሞ ።
ወይቤሎሙ ሰላም ለክሙ ።
እንዴት ሰነበታችሁ አስታረቅኋችሁ አላቸው ሁለት ሰዓት አሳልፎ መጥቶአልና እምድኅረ ሰሙን አለ።

፳፯ ወእምዝ ይቤሎ ለቶማስ አምጽእ አፅባዕተከ ዝየ ወርኢ እደውየ ወእገርየ ።

፳፯ ቶማስንም አለው ጣትህን ወደዚህ አምጣ እጄንም እይ ።
ወሀብ እዴከ ወአብእ ውስተ ገቦየ ወግሥሥ ።
እጅህን አምጣና ወደ ጐኔ አግባት ዳሰኝ ።
ወኢትኩን ናፋቂ አላ እመን ።
እመን እንጂ አትጠራጠር ።

፳፰ ወአውሥአ ቶማስ ።

፳፰ ቶማስም መለሰ ።
ወይቤሎ እግዚእየ ወአምላኪየ ። ጌታዬ አምላኬ ሆይ አለ ። ቢዳስሰው ከእሳት እንደገባ ጅማት አድርጎታል ። መዳሰሱን ሲያይ እግዚእየ ማቃጠሉን ሲያይ አምላኪየ አለ ።
ይህንም ሊቁ አንተ ዘቀዳሚ ወአንተ ዘይእዜ ብሎታል ፡ ገቦ መለኮቱን የዳሰሰች እጁ በሕያውነት ትኖራለች በህንድ አገር ከታቦት ጋራ ከመንበር ላይ ነው የምትኖር ባመት ባመት በመቤታችን በዓል በአስተርእዮ ሊያጥኑ ሲገቡ የሚሾመውን ወጥታ ቀኝ እጁን ትይዘዋለች ዓመት እንግልጦ ያርፋል ባመቱ ሊያጥኑ ሲገቡ ትይዘዋለች እንዲህ እያለች ትኖራለች ።

፳፱ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ እስመ ርኢከኒሁ አመንከኒ ።

፳፱ ጌታም አለው ቶማስ ሆይ ብታየኝ አመንክ ። እመ ርኢከኒሁ ብታየኝ ብያ አመንክ ።
ብፁዓንሰ እለ እንዘ ኢይሬእዩኒ የአምኑኒ ።
ንዑዳን ክቡራንስ ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ናቸው ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

፴ ወብዙኃተ ካልዓተ ተአምራተ ገብረ እግዚእ ኢየሱስ በቅድመ አርዳኢሁ ዘኢተጽሕፈ ውስተ ዝንቱ መጽሐፍ ።

፴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ተአምራት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ በሦስቱ የተጻፈ እንድም በመላው ያልተጻፈ በተአምረ ኢየሱስ የተጻፈ ።

፴፩ ወዝንቱሰ ዘተጽሕፈ እምኔሆን ከመ ትእመኑ አንትሙ ከመ ኢየሱስ ክርስቶስ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ። ዮሐ ፳፩፡፳፭
፴፩ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ እናንተ ታምኑ ዘንድ ከተአምራቱ ይህ ተጽፏል ።
ወእሚነክሙ ትረከቡ ሕይወተ በስመ ዚአሁ ።
ስሙ ሕይወት መድኃኒት እንደሆነ አምናችሁም የዘለዓለም ድኅነትን ታገኙ ዘንድ ።

ዘከመ አስተርአዮሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት በብሔረ ጥብርያዶስ ።

ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወእምዝ ካዕበ አስተርአዮሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ በብሔረ ጥብርያዶስ ።
፩ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥብርያዶስ ሁለተኛ ታያቸው ።
ወከመዝ አስተርእዮሙ ።
እንዲህ ታያቸው ።
፪ እንዘ ሀለዉ ኅቡረ ስምዖን ወቶማስ ዘይብልዎ ዲዲሞስ ወናትናኤል ዘቃና ወደቂቀ ዘብዴዎስ ።
፪ እኒህ ሁሉ ባንድነት ሳሉ ።
ወዓዲ ካልአን ፪ቱ እምውስተ አርዳኢሁ ።
ዳግመኛም ከሰብአ አርድዕት ሁለቱ ሉቃስና ኒቆዲሞስ ። አንድም ይሁዳና ያዕቆብ ባንድነት ሳሉ ታያቸው ።
፫ ወይቤሎሙ ስምዖን ጴጥሮስ አንሰ አሐውር ከመ ዓሥግር ዓሣ ።
፫ የለመደ ግብር በጅ አይልምና ጴጥሮስ ዓሣ ልይዝ እሄዳለሁ አላቸው ።
ወይቤልዎ ካልዓኒሁ አርዳእ ንሕነኒ ንመጽእ ምስሌከ
ባልንጀሮቹ እኛም ካንተ ጋራ እንሄዳለን አሉት
ወሖሩ ወዓርጉ ሐመረ ።
ሄደው በመርከብ ተጫኑ ።
ወአልቦ ዘአሥገሩ በይእቲ ሌሊተ ወኢምንተኒ ።
በዚያች ለሌሊት ምንም ምን የያዙት የለም ።
፬ ወጸቢሖ ይቀውም እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ሐይቅ ።
፬ ሲነጋ በነጋ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከወደብ ተቀምጦ ነበር ።
ወኢያእመሩ አርዳኢሁ ወኢያእመሩ ከመ እግዚእ ኢየሱስ ውእቱ ።
ደቀ መዛሙርቱ ግን ጌታ እንደሆነ ዐላወቁም ነበር ።
፭ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ደቂቅየ ቦኑ ብከሙ ዘንበልዕ ።
፭ ኢየሱስም አላቸው ልጆቼ የምንመገበው እንዳች አላችሁን ።
ወይቤልዎ አልቦ ። የለም አሉት ።
፮ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አውርዱ መሣግሪክሙ ኀበ ይምን ሐመር ወትረክቡ ብዙኀ ።
፮ መረባችሁን በቀኝ በኩል ጣሉት ብዙ ትይዛላችሁ አላቸው ።
ወይቤልዎ ሠራሕነ ኵላ ሌሊተ ።
ሌሊቱን ሁሉ ደከምን ።
ወአልቦ ዘአኀዝነ ወኢምንተኒ ።
ምንም ምን ያገኘነው ነገር የለም ።
ወበቃልከሰ ናወርድ ።
ብታዘን ግን አይሆንም አንልም አሉት ፤ ፍቅረ ቢጽን አስተምሯቸዋልና ።
ወአውረዱሙ መሣግሪሆሙ ስእኑ እንከ ስሒበ እምብዝኃ ዓሣት ዘተሠግረ ።
መረባቸውን ከጣሉት በኋላ ግን ከተያዘው ዓሣ ብዛት የተነሳ ስቦ ማውጣት ተሣናቸው ።

፯ ወይቤሎ ለጴጥሮስ ዝኩ ካልዕ ረድእ ዘያፈቅሮ እግዚእ ኢየሱስ እግዚእነ ውእቱ ።
፯ ባለሟሉ ዮሐንስ ጴጥሮስን ጌታችን እንጂ ነው አለው ።
ወሰሚዖ ስምዖን ጴጥሮስ ከመ እግዚእነ ውእቱ ነሥአ ዓራዘ ሰንዱነ ዘይትአጸፍ ቀነተ ውስተ ሐቌሁ ።
ስምዖን ጴጥሮስም ጌታ እንደ ሆነ በሰማ ጊዜ የእግር ነው ቢሉ ልብሱን ከፍ ከፍ አደረገ የዋና ነው ቢሉ ።
እስመ ዕራቁ ውእቱ ወተረወ ውስተ ባሕር ።
እራቁቱን ነበርና ወደ ባሕር ዘሎ ገባ ።
፰ ወካልዓንሰ አርዳዕ በሐመር በጽሑ ።
፰ ሌሎች ሐዋርያት ግን በመርከብ ሁነው ደረሱ ።
እስመ ኢኮኑ ርኁቃነ እምነ ምድር ዘእንበለ መጠነ ፪ኤ ፻ አመት ።
ከወደቡ ሁለት መቶ ክንድ ያህል ርቀው ነበርና ።
ወሖሩ እንዘ ይስሕቡ መሣግሪሆሙ ዘውስቴቶን ዓሣት ።
ዓሣ የተመላ መረባቸውን እየሳቡ ሄዱ ።
፱ ወወሪዶሙ ምድረ ።
፱ ወደ ምድር በደረሱ ጊዜ ፤
ረከቡ ፍሕመ ብቍጸ ።
ፍሕም መርቶ አዩ ።
ወዓሣ ጥቡሰ ፤
ዓሣ ተጠብሶ ።
ወማዕደ ሥሩዓ ፤
ማዕዱ ተሠርቶ አገኙ ፤ ዘእስተዳለውዎ ላእካኒሁ መንፈሳውያን እንዲል መላእክት አዘጋጅተውታል ።
፲ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ አምጽኡ እምዓሣት ዘአኀዝክሙ ይእዜ ።
፲ ኢየሱስም አላቸው አሁን ከያዛችሁት ዓሣ አምጡ ።

፲፩ ወዓርገ ስምዖን ጴጥሮስ ውስተ ሐመር ወሰሐበ መሥገርቶ ውስተ ምድር ።

፲፩ ጴጥሮስ ከመርከቡ ወጥቶ መረቡን ስቦ አወጣው ።
ወምሉእ ውእቱ ውስቴቱ ዓሣት ዓበይተ ፻ተ ወ፶ ወ፫ተ ።
መቶ አምሳ ሦስት ያህል ታላላቅ ዓሣ መልቶበት ነበር ።
ወእንዘ መጠነዝ ብዝኁ ኢተሰጠ ወኢተበትከ መሥገርቱ ።
ብዛቱ ይህን ያህል ሲሆን መረቡ አልተቀረጠም ፡

፲፪ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ንዑ ንምሳሕ ።

፲፪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ኑ እንብላ አላቸው ።
ወአልቦ ዘተህበለ እምአርዳኢሁ ከመ ይስአሎ ወይቤሎ መኑ አንተ ።
ከደቀ መዛሙርቱ ወገን አንተ ማነህ ብሎ ሊጠይቀው የወደደ የደፈረ የለም ።
እስመ አእመሩ ከመ እግዚእነ ውእቱ ፡
ጌታችን እንደሆነ ዐውቀዋልና ።

፲፫ ወመጽአ እግዚእ ኢየሱስ ወነሥአ ውእተ ኅብስተ ወወሀቦሙ ።

፲፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቦ በልቶ ኅብስቱን ሰጣቸው ።
ወእምዓሣሁኒ ከማሁ ።
ከዓሣውም ሰጣቸው ስልማዱ ጌታ ሲመገብ ስድስቱ ይቆማሉ ስድስቱ ይቀመጣሉ ፡ በዚህ ቀን ግን ዐሥራ እንዱ እንደቆሙ ተመግቧል ። ትንሣኤውን እንዲረዱት ምትሐት እንዳይደለ ለማጠየቅ መረብ የወንጌል ባሕር የዚህ ዓለም ምሳሌ ። በቀኝ በኩል ጣሉት ማለቱ ። ወንጌል በጥንተ ስብከት በቀኝ በኩል ነውና የተነገረች ። መቶ አምሳው ዓሣ እስከ ምጽአት የሚነሡ የምእመናን ምስቱ የሥላሴ ። መላእክት ካዘጋጁት ሐዋርያትም ካዘጋጁት በልቷል በርሱም በሐዋርያትም ስብከት ያመኑ ምእመናን አንድ እርሱን እንዲወርሱት ለማጠየቅ ።

፲፬ ወዝንቱ ሣልሱ እንዘ ያስተርእዮሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ እምድኅረ ተንሥአ እሙታን

፲፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሲታያቸው ይህ ሦስተኛው ነው ።

ዘከመ ተሠይመ ጴጥሮስ ርእሰ ሐዋርያት ።

፲፭ ወእምድኅረ መስሑ ይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ለስምዖን ጴጥሮስ ስምዖን ወልደ ዮና ታፈቅረኒኑ ፈድፋደ እምእሉ ።

፲፭ ምሳቸውን ከተመገቡ በኋላ ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን አለው ስምዖን ሆይ የዮና ልጅ እኒህ ከሚወዱኝ ይልቅ እኔህን ከምትወዳቸው ይልቅ አብልጠህ ትወደኛለህን አለው ።
ወይቤሎ እወ እግዚኦ ለሊከ ተአምር ከመ እን አፈቅረከ ።
አቤቱ እንድወድህ አንተ ታውቀዋለህ አለው ።
ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ረአይኬ አባግዕየ ።
በጎቼን ጠብቅ ማለት ለጊዜው ዐሥሩን ፍጻሜው ግን መላውን መምህራንን ጠብቅ አለው ።

፲፮ ወካዕበ ዳግመ ይቤሎ ኦ ስምዖን ወልደ ዮና ታፈቅረኒኑ

፲፮ ሁለተኛ የዮና ልጅ ስምዖን ትወደኛለህን አለው ።
ወይቤሎ እወ እግዚኦ አንተ ተአምር ከመ አነ አፈቅረከ ።
አቤቱ እኔ እንድወድህ አንተው ታውቀዋለህ አለው ።
ወይቤሎ ረአይኬ መሐስዕየ ።
ለጊዜው ሰብአ አርድዕትን ፍጻሜው ግን መላውን ጠብቅ አለው ።

፲፯ ወይቤሎ ሣልሰ ስምዖን ወልደ ዮና ታፈቅረኒኑ ።

፲፯ ሦስተኛ የዮና ልጅ ስምዖን ትወደኛለህን አለው ።
ወተከዘ ጴጥሮስ እስመ ይቤሎ ሣልሰ ታፈቅረኒኑ ።
ሦስት ጊዜ ስለ ጠየቀው ጴጥሮስ አዘነ ሦስት ጊዜ እንጂ ክጄው ነበርና በዚያ አነጻጽሮ እንዲህን አለኝ ብሎ ።
ወይቤሎ እወ እግዚእ ለሊከ ተአምር ኵሎ ወለሊከ ትጤይቅ ከመ አነ አፈቅረከ ።
አቤቱ እንድወድህስ አንተ ታውቃለህ አለው ።
ወይቤሎ ረአይኬ አባግዕትየ ። ለጊዜው ፴፮ ቅዱሳት አንስት ፡ ፍጻሜው ግን መላውን ጠብቅ አለው ፍቅሩን መማለጃ አድርጎ ሾሞታል ከጭቃ የወደቀውን ዕንቊ ወልውለው ሰንግለው ከቦታው እንዲያኖሩት ።

፲፰ አማን አማን እብለከሙ አመ ወሬዛ አንተ ለሊከ ትቅንት ሐቌከ ። ፪ ጴጥ ፩፡፲፬ ።

፲፰ ከእአምሮ ሕፃን በነበርክ ጊዜ ወገብ ልቡናህን በፍርሃት ዝናር ትታጠቃለህ ።
ወተሐውር ኀበ ፈቀድከ ።
ወደምትወደውም ሄደህ ነበርህ ። ወደወደድከው ማለት ኢየእምሮ ለዘትቤሊ ወደማለት ትሄዳለህ ።
ወእመሰ ልሕቀ ታነሥእ እደዊከ ፍጹመ ።
በእእምሮ በጐለመስህ ጊዜ ግን እጅህን ታነሣለህ ማለት ፍርሃትን ከልቡናህ ታርቃለህ እጅህን ለመስቀል ትዘረጋለህ ።

ወባዕድ ያቀንተከ ሐቌከ ።

ባዕድ ኔሮን ። አንድም ባዕድ መንፈስ ቅዱስ እንድትሰቀል ያደርግሃል ብዬ በውነት እነግርሃለሁ በግብርም በከብርም ባነዋወርም በባሕርይም ባዕድ ባነዋወርም በባሕርይም ባዕድ ነውና ባዕድ አለው

ወይወስደከ ኀበ ኢፈቀድከ ።

ትፈራው አትወደው ወደነበረ ሞት ይወስድሀል ፣ አንድም እመ ወሬዛ ብለህ መልስ ፡ በአእምሮ በጕለመስከ ጊዜ ወገብ ልቡናህን በጥብዓት ዝናር ትታጠቃለህ ወተሐውር እመውትኒ ምስሌከ ወኢ ይከህደከ ወደማለት ትሄዳለህ ወእመሰ ልህቀ አይ ለወጥም ።

፲፱ ወዘንተ ዘይቤ እንዘ ይኤምሮ በአይ ሞት ሀለዎ ይሰብሖ ለእግዚአብሔር ።

፲፱ በምን ሞት ሞቶ እግዚአብሔርን ያመሰግነው ዘንድ እንዳለው ሲያስረዳ ይህን ተናገረ አንድም ወዘንተ ዘይቤ ብለህ መልስ ይህን የተናገረ በምን ሞት ይሞት ዘንድ አለው ቢሉ በመስቀል ተሰቅሎ ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያስረዳ ነው ።

ወዘንተ ብሂሎ ይቤሎ ትልወኒ ይህን ተናግሮ ተከተለኝ በሞት ምሰለኝ አለው ።

፳ ወተመይጦ ስምዖን ጴጥሮስ ርእዮ ለዝኩ ካልዕ ረድእ ዘያፈቅሮ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይተልዎ ። የዮሐ፡፲፫ ፡ ፳፫ ።

፳ ጴጥሮስ ዘወር ብሎ ባለሟሉን ዮሐንስን ጌታን ሲከተል አየው ።

ወውእቱ ረድዕ ዘረፈቀ ዲበ እንግድዓሁ እንዘ ይድረሩ ።

እርሱም በእራት ጊዜ ባጠገቡ የተቀመጠው ነው ።

ወዘይቤሎ እግዚእ መኑ ውእቱ ዘያገብአከ ።

አቤቱ የሚያሲዝህ ማነው ብሎ የጠየቀው ነው ።

፳፩ ወኪያሁ ርእዮ ጴጥሮስ ይቤሎ ለእግዚእ ኢየሱስ እግዚኦ ዝኬ እፎ ።

፳፩ ጴጥሮስ እርሱን አይቶ ጌታን ይህስ እንደምን ይሁን አለው ባለጌ አያዝንም ስለገበረ ባልንጀራው እንጅ ስለቀረ እንዲሉ ።

፳፪ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ለጴጥሮስ እመኬ ፈቀድኩ የሃሉ እስከ ሶበ እመጽእ ሚላዕሌከ ።

፳፪ እኔ ከወደድኩ እስክመጣ ቢኖር አንተ ከርሱ ምን ነ ለህ አለው የግድግድ አመላለስ አንድም ነገር ለማስቆም ።

ወአንተሰ ትልወኒ ።

አንተስ ተከተለኝ ምሰለኝ ፡

፳፫ ወወፅአ ዝንቱ ነገር በኀበ አኃው ከመ ውእቱ ረድእ ኢይመውት ።

፳፫ እንዲህ ቢለው ሐዋርያት ዮሐንስ አይ ሞትም አሉ ።

ወባሕቱ እግዚእ ኢየሱስ ኢይቤሎ ኢይመውት ጌታ ግን አይሞትም አላለውም ።አላ ይቤ እመኬ ፈቀድኩ የሀሉ እስከ ሶበ እመጽእ ሚላዕሌከ ።እኔ ከወደድኩ እስክመጣ ቢኖር ምን አግዶህ አለው አንጂ አይሞትም አላለም ፡ ዮሐንስ ሞቷልን አል ሞተም ቢሉ አልሞተም ። ይህስ እንዳይሆን ሊቁ ከመቃብር ጴጥሮስ ወጳውሎስ ወዮሐንስ አሙራን ወከሡታን አሙንቱ ይላል ብሎ ሞቷል ፡ ይህም ሊታወቅ መላእከት መቃብሩን ቆፍረዋል ከመቃብሩ ገብቶ ሲጸልይ ደቀ መዝሙሩን ፋጊርን የኤፌሶንን ሰዎች በተማራችሁት ትምህርት ጸንታችሁ ኑሩ ብለህ ንገራቸው ብሎ ላከው ነግሮ ቢመለስ መቃብሩ የለፋ መስከ ሁኖ አጽፋን መቋሚያውን መነሣንሱን ከዳሩ አግኝቶታል ።

፳፬ ወዝንቱ ውእቱ ረድእ ዘኮነ ሰማዕተ በእንተዝ ።

፳፬ ይህ ደቀ መዝሙር ነው ስለዚህ ሥራ የመሰከረ ።

ወዘሂ ጸሐፈ በእንቲአሁ ዘንተ ።

የርሱን ነገር የጻፈ ይህ ዮሐንስ ነው ።

ወንሕነ ነአምር ከመ ጽድቅ ውእቱ ስምዑ ።

ምስክርነቱ እውነት እንደሆነ እኛ እናውቃለን ።

፳፭ ወዘንተ ገብረ እግዚእ ኢየሱስ ዮሐ.፳፩፡፳፭።

፳፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አደረገ ።

ወቦ ባዕዳትኒ ግብራት ዘገብረ እግዚእ ኢየሱስ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው ሌላም ተአምራት አለ ።

ወሶበ ፡ ተጽሕፈ ኵሉ በበ፩ዱ እምኢያገመሮ ዓለም ጥቀ መጻሕፍቲሁ ዘተጽሕፈ ።

እያንዳንዱ ቢጻፍ ሰማይ ምድር ሣጥን ቢሆኑባል ተወስኖም ነበር ። አንድም ጌታ ያደረገው ተአምራት እያንዳንዱ ቢጻፍ ሰማይና ምድር ፡ ስሌዳ አእባን መረመሚያ ። አብሀርት ቀለም ፡ አሥዕርት ፡ ዕፀዋት ብርዕ መላእከትና ደቂቀ አዳም ጸሐፍት ቢሆኑ ጽፈው ባልፈጸሙትም ነበር ። መልአ ጽሕፈተ ብሥራቱ ለዮሐንስ ሐዋርያ ወልደ ዘብዴዎስ ፩ዱ እም ፲ወ፪ቱ ሐዋርያት ካሥራ ፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ሐዋርያ የጻፈው ወንጌል ደረሰ ተፈጸመ ዘጸሐፎ በልሳነ ዮናኒ ለሰብእ ሀገረ ኤፌሶን እምድኅረ ዕርገቱ ለእግዚእነ በሥጋ ውስተ ሰማይ በ፴ ዓመት ። ጌታችን በሥጋ ወደ ሰማይ ባረገ በሠላሳ ዘመን በዮናኒ ቋንቋ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈው መበ፯ቱ ዓመተ መንግሥቱ ለኔሮን ቄሣር ንጉሠ ሮም። የሮም ንጉሥ ኔሮን በነገሠ በሰባት ዓመት ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ። እስኵምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው ። አሜን ።

ጉልቄ ምዕራፍ ዓቢይ ዘወንጌለ ዮሐንስ ።	የዮሐንስ ወንጌል የዐቢይ ምዕራፍ ቊጥር ።
ምዕራፍ ፩ ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ።	ያቃል በፊት የነበረው ነው ።
ም ፪ ወአመ ሣልስት ዕለት ከብካብ ኮነ ።	በሦስተኛው ቀን ሰርግ ተደረገ ።
ም ፫ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ እምፈሪሳውያን ዘስሙ ኒቆዲሞስ ።	ከፈሪሳውያን ወገን ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ ።
ም ፬ ወአእሚሮ እግዚእነ ከመ ሰምዑ ፈሪሳውያን ።	ፈሪሳውያን እንደሰሙ ጌታችን ዐውቆ ።
ም ፭ ወእምድኅረዝ ኮነ በበዓሎሙ ለአይሁድ።	አይሁድ በዓላቸውን በሚያከብሩበት ቀን ።
ም ፮ ወእምድኅረ ዝንቱ ሖረ ኢየሱስ ማዕዶተ ባሕረ ገሊላ ዘጥብርያዶስ ።	ከዚህ በኋላ ወደገሊላ ባሕር ማዶ ሄደ ።
ም ፯ ወእምድኅረ ዝንቱ ሖረ ኢየሱስ ውስተ ገሊላ ።	ከዚህ በኋላ ጌታ ወደ ገሊላ ሄደ ።
ም ፰ ወኢየሱስሰ ሖረ ውስተ ደብረ ዘይት።	ጌታም ወደ ደብረ ዘይት ሄደ ።
ም ፱ ወእንዘ የሐልፍ ኢየሱስ እምህየ ርእየ ብእሴ ዘዕውሩ ተወልደ ።	ጌታ ከዚያ አልፎ ሲሄድ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው አየ ።
ም ፲ አማን እብለክሙ ዘኢቦአ እንተ አንቀጽ ዐጸደ አባግዕ ።	በጎች ወደአሉበት በበር ያልገባ ።
ም ፲፩ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ ዘስሙ አልዓዛር ።	አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው ነበር ።
ም ፲፪ ወእምዝ ሖረ ኢየሱስ እምቅድመ ሰዱስ መዋዕል ዘፋሲካ ።	ጌታ ከስድስት ቀን አስቀድሞ ሄደ ።
ም ፲፫ ወእምቅድመ በዓለ ፋሲካ ።	ከበዓለ ፋሲካ አስቀድሞ ።
ም ፲፬ ኢይደንግፅክሙ ልብክሙ ።	ልባችሁ አይደንግጥባችሁ ።
ም ፲፭ አነ ውእቱ ሐረገ ወይን ዘጽድቅ ።	እውነተኛ የወይን ሐረግ እኔ ነኝ ።
ም ፲፮ ወዘንተ ነገርኩክሙ ከመ ኢትትዐቀፉ።	እንዳትጠራጠሩ ይህን ነገርኋቸው ።
ም ፲፯ ወዘንተ ነገረ ተናጊሮ አንሥአ አዕይንቲሁ ።	ይህን ተነጋግሮ ዐይኑን አቀና ።
ም ፲፰ ወዘንተ ብሂሎ ወፅአ ፈለገ አርዝ ።	ይህን ተናግሮ ወደዛፉ ወንዝ ሔደ ።
ም ፲፱ ወእምዝ ነሥአ ጲላጦስ ወቀሠፎ ።	ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ይዞ ገረፈው ።
ም ፳ ወበእሑድ ሰንበት ።	በመጀመሪያ ሰንበት ።
ም ፳፩ ወእምዝ አስተርአዮሙ ለአርዳኢሁ ።	ከዚህ በኋላ ለተማሪዎች ታያቸው ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ዮሐንስ ።		የዮሐንስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ከዊኖቱ ለቃል መለኮታዊ ። ወበእንተ ተፈንዎተ ዘዮሐንስ መጥምቅ ።	ምዕራፍ ፩ ቍጥር ፩	ስለ ቃል መለኮታዊነትና ስለ ዮሐንስ መላክ ።
በእንተ ስምዑ ለዮሐንስ መጥምቅ ።	ቍ ፲፱	ስለ ዮሐንስ ምስክርነት ።
በእንተ ቀዳማውያን አርድዕተ ኢየሱስ ።	ቍ ፴፭	ስለ መጀመሪያዎች የጌታ ተማሪዎች ።
በእንተ ዘከመ ተገብረ ከብካብ በቃና ዘገሊላ ።	ም ፪ ቍ ፩	በገሊላ አውራጃ በቃና ሰርግ ስለ ተደረገ ።
በእንተ ዘከመ ዐርገ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ።	ቍ ፲፪	ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ስለወጣ ።
በእንተ ዘከመ ተሰዱ ሠየጥ እምዙራብ ፡	ቍ ፲፫	የሚሸጡ ተምዙራብ ስለ ተሰደዱ ።
በእንተ ቀዳሚት ፋሲካ ዘኢየሱስ ።	ቍ ፳፫	ስለ መጀመሪያይቱ ፋሲካ ።
በእንተ ኢየሱስ ወኒቆዲሞስ	ም ፫ ቍ ፩	ስለ ጌታ ስለ ኒቆዲሞስ ።
በእንተ ዳግማዊ ስምዑ ለዮሐንስ	ቍ ፳፪	ስለ የዮሐንስ ሁለተኛ ምስክርነት ።
በእንተ ኢየሱስ ወሳምራዊት ።	ም ፬ ቍ ፩	ስለ ጌታና የሰማርያ ሴት ።
በእንተ ዘከመ አሕየዎ ኢየሱስ በገሊላ ለወልደ ንብረ ንጉሥ ።	ቍ ፵፫	ጌታ የንጉሥን ባሪያ ልጅ በገሊላ ስለ አዳነው ።
በእንተ ምጥማቃት ዘጽሩጸጥቄ ።	ም ፭ ቍ ፩	ስለ መጠመቂያ ።
በእንተ ዘከመ አስተዋደይዎ አይሁድ ለኢየሱስ ።	ቍ ፲	ጌታን አይሁድ ስለ አካሰሱት ።
በእንተ አብዝኖተ ኅብስት ወዓሣ ።	ም ፮ ቍ ፩	እንጀራውንና ዓሣውን ስለ አበረከተ ።
በእንተ ዘከመ ሖረ ኢየሱስ ዲበ ባሕር ።	ቍ ፲፮	ጌታ በባሕር ላይ ስለ ሄደ ።
በእንተ ዕቅፍት ወዕልወት ዘእምአርድዕተ ኢየሱስ ።	ቍ ፷	ከጌታ ተማሪዎች ስለ መሰናከል ፡
በእንተ ዘከመ ሖረ ኢየሱስ ኀበ በዓለ መጸለት ።	ም ፯ ቍ ፩	ጌታ ለመጸለት በዓል ስለ ሄደ ።
በእንተ ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ ገሃደ በእንተ ተፈንዎቱ መለኮታዊት ፡	ቍ ፲፬	ጌታ ስለ መለኮታዊ መላኩ ገልጦ ስለ ተናገረ ።
በእንተ ዘከመ ከሠተ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ።	ቍ ፴፯	ጌታ መንፈስ ቅዱስን ስለ ገለጠ ።
በእንተ ዘከመ ሐለዩ አይሁድ ላዕለ ኢየሱስ ዘዘዚአሆሙ ሐልዮታተ ።	ምዕራፍ ፯ ቍጥር ፵	በጌታ ላይ ልዩ ልዩ አሳብን አይሁድ ስለ አሰቡ ።
በእንተ ዘማዊት ብእሲት ።	ም ፰ ቍ ፩	ስለ ሴሰኛይቱ ሴት ።
በእንተ ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ ተፈንዎቶ መለኮታዊተ ።	ቍ ፲፪	መለኮታዊ መላኩን ጌታ ስለ ተናገረ ።
በእንተ ዘከመ ገሠጸ ኢየሱስ ትዝኅርቶሙ ለአይሁድ ።	ቍ ፴፫	ጌታ የአይሁድን ትዕቢታቸውን ስለ ገሠጸ ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ዮሐንስ					የዮሐንስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ዘከመ ፈወሶ ለዘዕ ውሩ ተወልደ ።	ም	፱	ቍ	፩	ዕውር ሆኖ የተወለደውን ስለ አዳነው ።
በእንተ ኖላዊ ኄር ፡	ም	፲	ቍ	፩	ስለ ቸር ጠባቂ እረኛ ።
በእንተ ዘከመ ሀሎ ኢየሱስ በበዓለ ሐድሶ ሕንፃ ።			ቍ	፳፪	ጌታ በሕንጸ መታደሻ በዓል ስለ ነበረ ።
በእንተ ጽልዕ ዘአይሁድ ላዕለ ኢየሱስ ።			ቍ	፴፩	በጌታ ላይ ስለ አይሁድ መጸላት ።
በእንተ ዘከመ አንሥኦ ኢየሱስ ለዓልዓዛር	ም	፲፩	ቍ	፩	ጌታ አልዓዛርን ስለ አሥነሣው ።
በእንተ ዘከመ ተማከሩ አይሁድ ይቅትልዎ ለኢየሱስ ።			ቍ	፵፯	ጌታን ሊገድሉት አይሁድ ስለ መከሩ ።
በእንተ ዘከመ ተግኅሠ ኢየሱስ እምኢየሩሳሌም ።			ቍ	፶፭	ጌታ ከኢየሩሳሌም ስለ ሔደ ።
በእንተ ድራር ዘቢታንያ ።	ም	፲፪	ቍ	፩	ስለ ቢታንያ እራት ።
በእንተ ዘከመ ገብአ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ።			ቍ	፲፪	ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ስለ ተመለሰ ።
በእንተ እምነቶሙ ለአረሚ ወኢአሚኖቶሙ ለአይሁድ ።			ቍ	፳	ስለ አረማውያን ማመንና ስለ አይሁድ አለማመን
በእንተ ተፍጻሜ ድራር ወሕፅበተ እገሪሆሙ ለሐዋርያት ።	ም	፲፫	ቍ	፩	ስለ መጨረሻው እራትና ስለ ሐዋርያት እግር መታጠብ ።
በእንተ ዘከመ አእመረ ኢየሱስ ዘያገብኦ ።			ቍ	፳፩	ጌታ የሚያሲዘውን ስለ ዐወቀ ።
በእንተ ዘከመ ተናገረ ኢየሱስ እምድኅረ ድራር ወዘከመ ተነበየ ኅዲጎት ዘሐዋርያት ።			ቍ	፴፩	ጌታ ከእራት በኋላ ስለተናገረና ስለሐዋርያት መተው።
በእንተ ፍሬያት ዘድኅነት።	ም	፲፬	ቍ	፩	ስለ መዳን ፍሬዎች ፡
በእንተ ሐረገ ወይን ወበእንተ አዕጹቂሁ ።	ምዕራፍ	፲፭	ቍጥር	፩	ስለ ወይን ሐረግ ስለ ጫፎቹ ።
በእንተ ዘከመ ይደልዎሙ ለአኃው ተፋቅሮት ።			ቍ	፲፪	ስለ ወንድሞች ፍቅር ።
በእንተ ጸሊዓ ዝንቱ ዓለም ።			ቍ	፲፰	ዓለምን ስለመጥላት ።
በእንተ ስደታት ።	ም	፲፮	ቍ	፩	ስለ መሰደድ ።
በእንተ ዘከመ አሰፈዎሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ።			ቍ	፯	ጌታ ለሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ስለ ሰጣቸው ።
በእንተ ተመይጦተ ኢየሱስ ውስተ ሰማይ ።			ቍ	፲፮	ጌታ ወደ ሰማይ ስለ ተመለሰ ።
በእንተ ዘከመ ተሰነአለ ኢየሱስ እምአርድእት ።			ቍ	፳፰	ጌታ ከተማሪዎቹ ስለ ተሰናበተ ።
በእንተ ዘከመ ጸለየ ኢየሱስ	ም	፲፯	ቍ	፩	ጌታ ስለ ጸለየ ።

መክሥተ አርእስት ዘወንጌለ ዮሐንስ ።			የዮሐንስ ወንጌል አርእስት ማውጫ ።
በእንተ ዘከመ ጸለየ ኢየሱስ በጌተሴማኒ ።	ም ፲፰	ቍ ፩	በጌቴሴማኒም ስለ ጸለየ ።
በእንተ ዘከመ አግብኦ ይሁዳ ለኢየሱስ ወዘከመ አኀዝዎ ለኢየሱስ ።		ቍ ፫	ጌታን ይሁዳ ስለ አሲያዘው ስለ ያዙት ።
በእንተ ዘከመ ቆመ ኢየሱስ ማእከለ ዐውድ		ቍ ፲፪	ጌታ በሸንጎ ስለ ቆመ ።
በእንተ ክህደተ ጴጥሮስ ።		ቍ ፲፭	ስለ ጴጥሮስ መካድ ።
በእንተ ተስእልዎ አይሁድ ለኢየሱስ ።		ቍ ፲፱	ጌታን አይሁድ ስለ ጠየቁት ።
በእንተ ክህደተ ጴጥሮስ ዳግመ		ቍ ፳፭	ስለ ጴጥሮስ ሁለተኛ መካድ ።
በእንተ ዘከመ ቆመ ኢየሱስ ቅድመ ጲላጦስ		ቍ ፳፰	ስለ ጌታ መቆም በጲላጦስ ፊት ።
በእንተ ዘከመ ኀረዩ በርባንሃ እምኔ ኢየሱስ ።		ቍ ፴፱	ከጌታ በርባንን ስለ መረጡ ።
በእንተ ዘከመ ይቤሎሙ ንዋ ብእሲ	ም ፲፱	ቍ ፩	ንጉሣችሁ እነሆ ስለ አላቸው ።
በእንተ ዘከመ በጽሐ ኢየሱስ ውስተ ቀራንዮ ።		ቍ ፲፯	ጌታ ቀራንዮ ስለ ደረሰ ።
በእንተ ዘከመ ቆሙ ማርያም ወዮሐንስ በታሕተ መስቀል ።		ቍ ፳፭	ማርያምና ዮሐንስ ከመስቀል እግር ስለ ቆሙ ።
በእንተ ገዐሩ ወሞቱ ለኢየሱስ ።		ቍ ፳፰	ስለ ጌታ ጩኸትና ሞት ።
በእንተ ዘከመ ተቀብረ ኢየሱስ ።		ቍ ፴፩	ጌታ ስለ ተቀበረ ።
በእንተ ዘከመ ሖሩ መግደላዊት ወጴጥሮስ ወዮሐንስ ውስተ መቃብር ።	ምዕራፍ ፳	ቍ ፩	ጴጥሮስና ዮሐንስ መግደላዊት ወደ መቃብር ስለ ሔዱ ።
በእንተ ዘከመ አስተርአያ ለማርያም መግደላዊት		ቍ ፲፩	ለመግደላዊት ማርያም ስለ ታየት ።
በእንተ ዘከመ አስተርአዮሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት		ቍ ፲፱	ጌታ ለሐዋርያት ስለ ታያቸው ።
በእንተ ዘከመ ተጠየቀ ቶማስ		ቍ ፳፬	ቶማስ ስለ ተረዳ ።
በእንተ ዘከመ አስተርአዮሙ ኢየሱስ ለሐዋርያት በጥብርያዶስ ።	ም ፳፩	ቍ ፩	ጌታ በጥብርያዶስ ለሐዋርያት ስለ ተገለጠላቸው ።
በእንተ ዘከመ ተሰየመ ጴጥሮስ ርእሰ ሐዋርያ ።		ቍ ፲፭	ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ ስለ ተሾመ ።

መጀመሪያው ሠንጠረዥ አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ማርቆስ		ሉቃስ		ዮሐንስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	
፫	፫	፩	፫	፫	፬	፩	፳፫	ቃለ ዓዋዲ ።
	፲፩		፰		፲፮		፳፮	አንስ አጠምቀክሙ ።
	፬		፮		፬		፯	ዘዮሐንስ ።
	፲፫		፱		፲፱		፲፱	ዘዮሐንስ ።
	፩		፬		፫		፴፮	ዘዮሐንስ ።
	፲፮		፲		፳፪		፴፪	ወወረደ መንፈስ ቅዱስ ።
፬	፲፪		፲፬	፬	፲፬		፵፫	ተማኅወ ውስተ ገሊላ ።
	፳፬		፳፰	፭	፲፭	፬	፵፭	ወተሰምዓ ነገሩ ።
	፳፭	፫	፯		፲፯		፵፭	ወተለውዎ ብዙኃን ሰብእ ።
፱	፪	፪	፫		፲፰	፭	፭	በእንተ መፃጉዕ ።
፲	፲፯	፲፫	፱	፳፩	፲፪	፲፮	፪	ወይወስዱክሙ አዕዋዳተ ።
	፴፫	፰	፴፰	፱	፳፮	፲፪	፵፰	ወዘሰ ክሕደኒ በቅድመ ሰብእ ።
፯	፳፬		፴፭	፮	፵፯	፭	፳፬	ዘይሰምዕ ቃልየ ።
፲፫	፳፫		፳፭		፵፰	፲፬	፳፩	ዘቦቱ ትእዛዝየ ።
	፲፱	፬	፳፫		፵፱		፳፫	ወዘኒ ሰምዓ ቃልየ ።
	፲፫		፲፪	፰	፲	፲፪	፵	ያሬ አዕይንቲሆሙ ።
	፶፭	፮	፫	፬	፳፪	፮	፵፪	አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልደ ዮሴፍ ።
	፶፯		፬		፳፬	፬	፵፬	ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ።
፲፬	፲፭	፮	፴፭	፱	፲፪	፮	፱	በእንተ ኃምስ ኅብስት ።
፲፮	፲፮		፳፱		፳		፷፱	አንተ ውእቱ ክርስቶስ ።
፳፩	፩	፲፩	፩	፲፱	፳፱	፲፪	፲፫	ሆሣዕና ።
	፲፪		፲፭		፵፭	፪	፲፬	ወሰደደ እምኩራብ ።
	፲፯		፲፰	፳	፲፭	፯	፴፪	ወፈቀዱ የአኃዝዎ ።
፳፩	፵፮	፲፪	፲፪		፲፱		፵፬	ወፈቀዱ የአኃዝዎ ።
፳፬	፱	፲፫	፲፫	፳፩	፲፯	፲፭	፲፱	ወኵሉ ይጸልዓክሙ በእንተ ስምየ ።
፳፮	፪	፲፬	፩	፳፪	፩	፲፪	፩	እስከ ፪ኤ መዋዕል ይከውን ፋሲካ ።
	፲፯		፲፪		፯	፲፩	፶፭	ፋሲካ ።
	፯		፫	፯	፴፯		፫	በእንተ ዘቀብዓቶ ዕፍረተ ።
	፳፩		፲፰	፳፪	፳፩	፲፫	፳፩	ከመ ፩ዱ ያገብአኒ ።
	፳፪		፲፱		፳፫		፳፪	ወይቤሉ አነኑ እንጋ እግዚኦ ።
፳፮	፳፮	፲፬	፳፪	፳፪	፲፱	፲፫	፳፮	ወእንዘ ይበልዑ ነሥአ ።
	፳፯		፳፫		፳		፳፯	ዝኅብስት ።
	፴፫		፳፱		፴፫		፴፯	ሰእመ ኵሎሙ ክሕዱከ ።
	፴፬		፴		፴፬		፴፰	ሥልሰ ትክሕደኒ ።
	፴፮		፴፪		፴፱	፲፰	፩	ወሖረ ዐጸደ ወይን ።
	፴፱		፴፮		፵፪	፲፪	፳፯	ወባሕቱ ፈቃደ ዚአከ ለይኩን ።
	፵፪		፴፱		፵፪		፳፯	አኮ ከመ እግበር ፈቃድየ ።
	፵፫		፵		፵፭	፲፰	፪	ወረከቦሙ እንዘ ይነውሙ ።
	፵፰		፵፬		፵፯		፫	የአኀዝዎ ።
	፶		፵፮		፵፰		፬	የአኀዝዎ ።
	፶፩		፵፯		፶		፲	ወመልሐ መጥባሕቶ ።
	፶፭		፵፰		፶፪		፳	ወኵሎ እሚረ እሜህር ።
	፶፯		፶፫		፶፬		፲፪	አኀዝዎ ወወሰድዎ ።
	፶፰		፶፬		፶፬		፲፭	ወተለዎ ጴጥሮስ ።
	፷፬		፷፪		፷፱		፶፩	ወትሬእይዎ ።
	፷፯		፷፭		፷፫		፳፪	ወይጸፍዕዎ ገጸ ።

መጀመሪያው ሠንጠረዥ አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ማርቆስ		ሉቃስ		ዮሐንስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	
	፶፰		፶፬		፶፭		፳፭	ወሀሎ ጴጥሮስ ።
	፷፱		፷፮		፶፮		፳፮	ወቆመ ጴጥሮስ አፍአ ።
	፸፩		፷፱		፶፰		፲፯	ወረከበቶ ካልዕት ።
	፸፬		፸፪		፷		፳፯	ወሶቤሃ ነቀወ ።
፳፯	፪	፲፭	፩	፳፫	፩		፳፰	ወወሰድዎ ኀበ ጲላጦስ ።
	፲፩		፪		፫		፳፱	ወሐተቶ መስፍን ።
	፲፩		፪		፫		፴፯	ወይቤሎ አንተ ትቤ ።
	፲፮		፯		፲፰		፵	በእንተ በርባን ።
	፳		፲፩		፳፩		፵	ወሆከምዎሙ ።
	፳፩		፲፪		፳		፴፱	መኑ ትፈቅዱ ።
	፴፩		፳		፳፭	፲፱	፲፮	ወወሰድዎ ይቅትልዎ ።
	፴፪		፳፩		፳፮		፲፯	ወአበጥዎ ይጹር ።
	፴፭		፳፬		፴፬		፳፫	ወተካፈሉ አልባሲሁ ።
	፴፯		፳፮		፴፰		፲፱	ወአንበሩ ጽሒፎሙ ።
	፴፰		፳፯		፴፫		፲፰	ወእምዝ ሰቀሉ ።
	፵፮		፴፬		፵፬		፳፱	ወጊዜ ተስዓቱ ሰዓት ።
	፶		፴፯		፵፮		፴	ወጸርሐ ካዕበ ።
	፶፯		፵፪		፶		፴፩	ወመስዮ መጽአ ።
፳፯	፶፰	፲፭	፵፭	፳፫	፶፪	፲፱	፴፰	ወአዘዘ ጲላጦስ ።
	፶፱		፵፮		፶፫		፵	ወነሥኦ ዮሴፍ ።
፳፰	፩	፲፮	፩	፳፬	፩	፳	፩	ወሠርከ ሰንበት ።
	፪		፪		፪		፩	በእንተ እንስት ።
	፪		፭		፬		፲፪	ወመልአከ እግዚአብሔር ወረደ ።
	፬		፮		፭		፲፫	ወኮኑ ከመ አብድንት ።

ሁለተኛው ሰንጠረዥ ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ማርቆስ		ሉቃስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	
፬	፩	፩	፲፪	፬	፩	ወእምዝ መንፈስ ወሰዶ ገዳመ ።
	፲፱		፲፯	፭	፲	ወይቤሎሙ ንዑ ትልዉኒ ።
፭	፲፫	፱	፵፱	፲፬	፴፬	አንትሙ ውእቱ ጼው ለምድር ።
	፲፭	፬	፳፩	፰	፲፮	ወኢየኀትዉ ማኅቶተ ።
	፲፭		፳፪		፲፯	አልቦ ዘያሐቱ ።
፯	፪		፳፬	፮	፴፰	ወበመሥፈርት ዘሠፈርክሙ ።
	፳፰		፳፪	፬	፴፪	ወአንከሩ ምህሮቶ ።
	፳፰		፳፪		፳፪	ወአንከርዎ ማዕማዓ አፉሁ ።
፰	፪	፩	፵	፭	፲፪	ወናሁ ዘለምጽ ቀርበ ።
	፲፬		፴	፬	፴፰	ወረከባ ለሐማተ ጴጥሮስ ።
	፲፰	፬	፴፭	፰	፳፪	ወይቤሎሙ ንዕዱ ማዕዶተ ።
	፳፰	፭	፩		፳፮	ወበጺሖ ማዕዶተ ጌርጌሴኖን ።
፱	፪	፪	፫	፭	፲፰	ወአምጽኡ መጻጕዓ ።
	፱		፲፬		፳፯	ወረከበ ብእሴ መጸብሐዌ ።
	፲		፲፭		፳፱	ወእንዘ ይረፍቅ ውስተ ቤት ስምዖን ።
	፲፪		፲፯		፴፩	ሕሙማን ይፈቅድዎ ለዓቃቤ ሥራይ ።
፱	፲፰	፭	፳፪	፰	፵፩	ወመጽአ ፩ መኰንን ።
	፴፬	፫	፳፪	፲፩	፲፭	በመልእክቶሙ ለአጋንንት ያወፅኦሙ ።

ሁለተኛው ሠንጠረዥ ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ማርቆስ		ሉቃስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	
፲	፩		፲፫	፮	፲፫	ወጸውዖሙ ለ፲ወ፪ቱ ።
	፪		፲፮		፲፬	ወዝ ውእቱ አስማቲሆሙ ።
	፭		፲፬	፲	፩	ወፈነዎሙ ይስብኩ ።
	፱	፮	፰		፬	ኢትጹሩ ቍናማተ ።
	፲፩		፲		፰	ወውስተ ሀገር ኀበ ቦእክሙ ።
	፲፪		፲		፮	ወሶበ ትበውኡ ውስተ ቤት ።
	፲፬		፲፩		፲	ንግፉ ጸበለ አገሪክሙ ።
	፲፬		፲፩		፲፩	ወወፂአክሙ አፍአ ።
	፲፱	፲፫	፲፩	፲፪	፲፩	ወሶበ ይትባጽሑክሙ ።
	፲፱		፲፩		፲፪	ኢተሐልዩ ዘትብሉ ።
	፳፮	፬	፳፪	፰	፲፯	እስመ አልቦ ክዱን ።
	፴፫	፰	፴፰	፲፪	፱	ወዘሰ ክሕደኒ ።
፲፩	፪	፪	፲፰	፯	፳፬	ወሶበ ሰምዓ ዮሐንስ ።
፲፪	፩		፳፫	፮	፩	ወበውእቱ መዋዕል ።
	፰		፳፰		፭	እስመ እግዚአ ውእቱ ለሰንበት ።
	፳፬	፫	፳፪	፲፩	፲፭	በብዔል ዜቡል ።
	፳፭		፳፬		፲፯	ኵላ መንግሥት ።
	፴፩		፳፰	፲፪	፲	ኵሉ ኃጢአት ወጽርፈት ።
	፵፮		፴፩	፰	፲፱	መጽኡ ኀቤሁ እሙ ወአኀዊሁ ።
፲፫	፫	፬	፫		፭	ናሁ ወፅአ ይዝራዕ ።
	፴፩		፴፩	፲፫	፲፱	ትመስል ሕጠተ ሰናፔ ።
	፴፮		፲፫	፰	፰	ስምዑ ምሳሌሁ ለዘይዘርእ ።
፲፬	፩	፮	፲፬	፱	፯	ወሰሚዖ ሄሮድስ ።
	፬		፲፰	፫	፲፱	እስመ ይቤሎ ዮሐንስ ።
	፳፫		፵፮	፮	፲፪	ወዓርገ ደብረ ይጸሊ ።
	፴፬		፶፫	፭	፩	ወበጽሑ ምድረ ጌንሴሬጥ ።
፲፮	፮	፰	፲፭	፲፪	፩	ዑቁ ወተዓቀቡ ።
	፳		፲፰	፱	፳፩	ወገሠጾሙ ለአርዳኢሁ ።
	፳፩		፴፩		፳፪	ወብዙኃ የሐምምዎ ።
	፳፬		፴፬		፳፫	ዘይፈቅድ ይትልወኒ ።
	፳፰		፴፱		፳፯	ሀሰዉ ዝየ እምእለ ይቀውሙ ።
፲፯	፲፭	፱	፲፯		፵	እምጸአክዎ ለወልድየ ።
፲፯	፳፩	፱	፴	፱	፵፬	ሀለዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው ።
፲፰	፩		፴፫		፵፮	ወተበሃሉ መኑ የዓቢ ።
	፪		፴፮	፲፰	፲፭	ወጸውዓ ሕፃነ ።
	፮		፵፪	፲፯	፪	ይኄይስ ይእሰሩ ማኅረፀ አድግ ።
፲፱	፱	፲	፲፩	፲፮	፲፰	ወኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ ።
	፲፫		፲፫	፲፰	፲፭	ወአምጽኡ ሕፃናተ ።
	፲፮		፲፯		፲፰	ሊቅ ኄር ምንተ እግበር ።
	፲፯		፲፰		፲፱	ምንተ ትብለኒ ኄር ።
	፳፩		፳፩		፳፪	ወእመሰ ፍጹመ ትኩን ።
	፳፪		፳፪		፳፫	ወሰሚዖ ሖረ ትኩዞ ።
	፳፱		፳፱		፳፱	ወኵሉ ዘየኀድግ ።
	፴		፴፩	፲፫	፴	ወብዙኃን ቀደምት ።
፳	፲፯		፴፫	፲፰	፴፩	ናሁ ነዓርግ ኢየሩሳሌም ።
	፳፭		፵፪	፳፪	፳፭	መመላእክቲሆሙ ይኲንንዎሙ ።

ሁለተኛው ሠንጠረዥ ምስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስ የሚተባበሩበት ፨

ማቴዎስ		ማርቆስ		ሉቃስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	
	፴		፵፮	፲፰	፭	ወወጺኦ እምኢያሪሆ ፨
፳፩	፩	፲፩	፩		፳፱	ወበጺሖ ቤተ ፋጌ ፨
	፪		፪		፴	ወረከቡ ዕዋለ እሡረ ፨
	፳፫		፳፰	፳	፪	በመባሕተ መኑ ፨
	፴፫	፲፪	፩		፱	ብእሲ ተከለ ወይነ ፨
	፵፭		፲፪		፲፱	ወእእመሩ እምሳላቲሁ ፨
፳፪	፲፭		፲፫		፳	ወፈነዉ ከመ ያስሕትዎ ቤቃሉ ፨
	፵፪		፴፭		፵፩	ወይቤልዎ ወልደ ዳዊት ፨
	፵፮		፴፬		፵	ወእልቦ ዘተሃበለ ፨
፳፫	፮		፴፱		፵፮	ወነቢረ ፍጽም ፨
	፮	፲፪	፴፰		፵፮	ዑቁ እምጸሐፍት ፨
፳፬	፩	፲፫	፩	፳፩	፭	ወእርአይዎ ንድቀ ሕንጸሁ ፨
	፫		፫		፯	ኢይትኀደግ ዝየ እብን ፨
	፫	፬			፯	ማዕዜ ይከውን ዝንቱ ፨
	፲፯		፲፭		፴፩	ወይእተ እሚረ ይጕዩ እለ ውስተ ፨
	፲፱		፲፯		፳፫	እሌሎን ለፅኑሳት ፨
	፳፩		፲፱		፳፫	እስመ ይከውን ዐቢይ ሕማም ፨
	፳፫		፳፩	፲፯	፳፫	ነዋ ሀሎ ዝየ ክርስቶስ ፨
	፳፱	፳፬		፳፭	፳፭	ፀሐይኒ ይጸልም ፨
	፴		፳፮		፳፯	እሚሃ ይሬእይዎ ፨
፳፬	፴፪	፲፫	፳፰	፳፩	፳፱	እምበለስ እእምሩ እምሳሊሁ ፨
	፵፪		፴፫		፴፮	ትጉሁ እንከ ፨
፳፭	፲፬		፴፬	፲፱	፲፪	ወጸውኦ እግብርቲሁ ፨
	፳፱	፬	፳፭		፳፮	እስመ ለዘቦ ይሁብዎ ፨
፳፮	፲፬	፲፬	፲	፳፪	፫	ወእምዝ ሖረ አስቆሮታዊ ይሁዳ ፨
	፳፫		፳		፳፩	ዘያወርድ እዴሁ ፨
	፳፬		፳፩		፳፪	እሌ ሎቱ ለውእቱ ብእሲ ፨
	፳፮		፳፪		፲፱	ወነሥአ ኅብስተ ፨
	፳፯		፳፫		፳	ወከማሁ ጽዋዐኒ ፨
	፵		፴፯		፵፭	ወረከቦሙ እንዘ ይነውሙ ፨
	፵፩		፴፰		፵፮	ትጉሁ ወጸልዩ ፨
	፵፰		፵፬		፵፯	ወወሀቦሙ ትእምርተ ፨
	፶		፵፯		፵፱	በስኢምኑ ታገብእ ፨
	፶፭		፵፰		፶፪	ከመ ሠራቂ መጻእክሙ ፨
	፷፭		፷፬		፸፩	ወናሁ ስማዕክሙ ጽርፈቶ ፨
	፷		፶፯	፳፫	፩	ወቦ እለ ተንሥኡ ስማዕተ ሐሰት ፨
	፸፭		፸፪	፳፪	፷፩	ወተዘከረ ጴጥሮስ ቃሎ ፨
፳፯	፩	፲፭	፩		፷፮	ወጸቢሖ ተማከሩ ፨
	፲፭		፮	፳፫	፲፯	ወቦ ዘያለምድ ፨
	፴፱		፳፱		፴፭	ወእለሂ የኀልፉ ይፀርፉ ፨
	፵፩		፴፩		፴፭	ወከማሁ ሊቃነ ካህናትኒ ፨
	፵፬		፴፪		፴፱	ወከማሁ ፈያትኒ ፨
	፵፭		፴፫		፵፬	ወኮነ ጽልመት ውስተ ኵሉ ፨
	፶		፴፯		፵፮	ወጸርሐ በዓቢይ ቃል ፨
	፶፩		፴፰		፵፭	ወተሰጠ መንጠላዕተ ምኵራብ ፨
	፶፬		፴፱		፵፯	ወመኰንነ ፻ሰ ፨

ሁለተኛው ሠንጠረዥ ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ማርቆስ		ሉቃስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	
፳፰	፭	፲፮	፮	፳፬	፭	ወይቤሎን ለአንስት ።
	፰		፰		፱	ወወፅአ ፍጡነ ወሖራ እልክቱ ።

ሦስተኛ ሠንጠረዥ ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ሉቃስ ዮሐንስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ሉቃስ		ዮሐንስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	
፩	፩	፩	፳፮	፩	፲፩	ነገረ ልደቱ ።
	፲፰	፪	፮		፲፬	ዘኒ ከማሁ ።
፫	፩	፫	፫		፲፱	ወበውእቱ መዋዕል በጽሐ ዮሐንስ ።
	፲፫		፲፱		፴፭	ዘኒ ዘዮሐንስ ።
፯	፳፩	፮	፵፮	፲፫	፲፫	እኮ ኵሉ ዘይብለኒ ።
፰	፭	፯	፪	፬	፵፮	መጽአ ኀቤሁ መስፍነ ምእት ።
፲	፳፬	፮	፵	፲፫	፲፮	አልቦ ረድእ ዘየዓቢ እምሊቁ ።
	፴፱	፲፯	፴፫	፲፪	፳፭	ዘረከባ ለነፍሱ ።
፲፩	፳፯	፲	፳፪		፴፫	ኵሉ ተውኅበኒ ።
	፳፯		፳፪	፫	፴፭	ወኵሎ አወፈዮ ።
	፳፰		፳፫	፲፮	፲፭	ወኵሎ ዘቦ ለአቡየ ።
	፳፯		፳፩	፮	፵፮	ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ ።
፫	፲፯	፱	፵፭	፭	፴፯	ወራእዮሚ ኢርኢክሙ ።
	፲፯	፲፫	፳፯	፰	፶፭	ዘኢተአምርዎ አንትሙ ።
፳፩	፴፪	፲	፲፯		፲፱	ኢያየኑ ተአምሩ ።
	፵፭	፳	፱		፳፯	ወኢያእመሩ ከመ በእንተ አብ ይቤሎሙ ።
፲፩	፳፮	፲	፳፩	፲፭	፳፩	እስመ ኢያእምርዎ ለዘፈነወኒ ።
	፳፯		፳፪	፲፯	፳፭	ወዓለምሰ ኢያእመረከ ።
	፳፯		፳፪	፰	፶፭	አንሰ አአምሮ ለአብ ።
፱	፲፪		፳፫	፲፩	፶፬	ወተግኅሠ እምህየ ።

አራተኛ ሠንጠረዥ ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ዮሐንስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ማርቆስ		ዮሐንስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	ም	ቍ	
፬	፲፪	፩	፲፬	፫	፳፬	ወሰሚዖ ከመ አግብዎ ለዮሐንስ ።
፲፪	፲፬	፫	፮	፭	፲፰	ተማከሩ ከመ ይቅትልዎ ።
	፲፭		፮	፯	፵፬	ወፈቀዱ ከመ የአኀዝዎ ።
፰	፲፮	፩	፴፪		፲፮	ወምሴተ ከዊኖ ።
፱	፴፫	፩	፳፯		፲፭	ወአንከርዎ ሕዝብ ።
፲፪	፴፰	፰	፲፩	፮	፴	ምንተ ትእምርተ ታርኢ ።
፲፮	፩		፲፪		፴	ምንተ ተእምረ ትገብር ።
፳	፳፮	፲	፵፫	፲፫	፲፭	ይኩንክሙ ንብረ ።
፳፩	፳፪	፲፩	፳፫	፲፬	፲፫	ወኵሎ ዘሰአልክሙ ።
	፳፪		፳፬	፲፭	፯	ይከውን ለክሙ ።
፯	፯		፳፬	፲፮	፳፫	ዘሰአልክምዎ ለአብ በስምየ ።
፳፮	፳፩	፲፬	፲፰	፲፫	፳፩	፩ እምኔክሙ ያገብአኒ ።
	፴፩		፳፯	፲፮	፴፪	ኵልክሙ ትክሕዱኒ ።
	፴፰		፴፬	፲፪	፳፯	ተከዘት ነፍስየ ።
	፵፩		፴፰	፲፫	፪	እስመ መንፈስ ይፈቅድ ።
	፵፮		፵፪		፩	ናሁ በጽሐ ጊዜሁ ለዘያገብአኒ ።

	፶፰		፶፬		፲፭	ወተለዎ ጴጥሮስ ።
፳፯	፲፬		፷፩		፳፩	ወአልቦ ዘተሠጥዎሙ ።
	፲፮	፲፭	፯		፴፱	ወሀሎ ሙቁሕ ዘስሙ በርባን ።
	፳፮		፲፭		፵	እሕየወ ሎሙ በርባንሃ ።
	፳፮		፲፭	፲፱	፩	ወቀሰፎ ለእግዚእ ኢየሱስ ።
	፴፬		፳፫		፳፱	ወወሀብዎ ይስተይ ብሒዓ ።
	፳፯		፲፮		፪	ወእምዝ ተመጠውዎ ሠገራ ።

እምስተኛው ሠንጠረዥ ሁለቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ሉቃስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ሉቃስ		
ም	ቁ	ም	ቁ	
፪	፲፫	፪	፱	ናሁ መልአከ እግዚአብሔር ።
፫	፲	፫	፱	ናሁ ወድአ ተሠይመ ።
	፲፪		፲፯	ዘመሥኤ ውስተ እዴሁ ።
	፲፫		፳፩	እሜሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ።
፬	፫	፬	፪	ወእምዝ ቀርበ ዘያሜክሮ ።
፭	፫	፮	፳	ብፁዓን ነዳያን ።
፭	፬	፮	፳፩	ብፁዓን እለ ይላሕዉ ።
	፮		፳፩	ብፁዓን እለ ይርህቡ ።
	፲፩		፳፪	ብፁዓን አንትሙ ሶበ ይጼዕሉክሙ ።
	፲፰	፲፮	፲፯	እስከ አመ የኀልፍ ሰማይ ።
	፳፭	፲፪	፶፰	ኩን ጠቢበ በዕድውከ ።
	፴፱	፮	፳፱	ወለዘኒ ጸፍዓከ ።
	፵፬		፴፭	አፍቅሩ ጸላዕተክሙ ።
	፵፮		፴፪	ወእመሰ ዘአፍቀረክሙ ።
፮	፯	፲፩	፪	ወእንዘ ትጼልዩ ።
	፲፱	፲፪	፴፫	ኢትዝግቡ መዝገበ ።
	፳፪	፲፩	፴፬	ማኅቶቱ ለሥጋከ ።
	፳፬	፲፮	፲፫	አልቦ ዘይክል ተቀንዮ ለ፪ኤ ።
	፳፭	፲፪	፳፪	ወበእንተዝ ኢትትክዙ ለሥጋክሙ ዘትበልዑ።
፯	፫	፮	፵፩	ምንተ ትሬኢ ኀሠረ ።
	፯	፲፩	፱	ሰአሉ ወይትወሀበክሙ ።
	፲፪	፮	፴፩	ኵሎኬ ዘትፈቅዱ ።
	፲፫	፲፫	፳፬	ባኡ እንተ ፀባብ አንቀጽ ።
	፲፮	፮	፵፬	ወእምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ ።
	፲፮		፵፬	ይቀሥሙሁ እምእስዋክ አስካለ ።
	፲፰		፵፫	ኢይክል ዕፅ ሠናይ ።
	፳፪		፵፮	ወብዙኃን ይብሉኒ በይእቲ ዕለት ።
	፳፬		፵፯	ወኵሉ ዘይሰምዕ ቃልየ ።
፰	፲፩	፲፫	፳፰	ወይረፍቁ ውስተ ሕፅነ አብርሃም ።
	፳	፱	፶፰	ለቈናጽልኒ ግበብ በሙ ።
፱	፴፯	፲	፪	ማዕረሩሰ ብዙኅ ።
፲	፲፩		፰	ወውስቴ ሀገር እንተ ቦእክሙ ።
	፲፮		፫	ወናሁ እፌንወክሙ ።
	፳፯	፲፪	፫	ዘነገርኩክሙ ውስተ ጽልመት ።
	፴፬		፶፩	ሰላመ ኢያምጻእኩ ።
	፴፯	፲፬	፳፮	ዘያፈቅር አባሁ ወእሞ ።
፲፩	፲	፯	፳፯	ወናሁ እፌኑ መልአኪየ ።
	፲፩		፳፰	ኢተንሥአ እምትውልደ አንስት ።
	፲፪	፲፮	፲፮	ትትገፋዕ መንግሥተ ሰማያት ።

እምስተኛው ሠንጠረዥ ሁለቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ሉቃስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ሉቃስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	
	፲፮	፯	፴፩	በመኑ አስተማስሎ ።
፲፩	፳፩	፲	፲፫	አሌ ለኪ ኮራዚ ።
	፳፭		፳፩	አእምነከ አባ ።
፲፪	፲፩	፲፬	፭	ይከውንሁ በሰንበት ።
	፮		፮	ዝኒ ከማሁ ።
	፳፪	፲፩	፲፬	ወእምጽኡ ሎቱ በሐመ ።
	፴፭	፮	፵፭	ኄር ብእሲ እምሠናይ መዝገበ ልቡ ።
	፴፰	፲፩	፳፱	ንፈቅድ እምኀቤከ ትእምርተ ።
	፴፱		፳፱	ወትእምርትሰ ኢይትወሀባ ።
	፵፫		፳፬	ወእምከመ ወፅአ መንፈስ ርኩስ ።
፲፫	፲፪	፰	፲፰	እስመ ለዘቦ ይሁብዎ ።
	፲፮	፲	፳፫	ወለከሙሰ ብፁዓት ።
	፴፫	፲፫	፳	ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብሑዓ ።
፲፭	፲፬	፮	፴፱	ዕውር ዕውረ ለእመ መርሐ ።
፲፮	፪	፲፪	፶፬	እምከመ መስየ ።
፲፯	፳	፲፯	፮	እመ ብከሙ ሃይማኖት ።
፲፰	፲፪	፲፭	፬	ዘቦ ፻ አባግዐ ።
	፲፭		፫	ለእመ አበሰ ለከ ።
	፲፭		፬	እስከ ሰብዕኑ ።
፲፱	፳፰	፳፪	፴	ወአንትሙኒ ትነብሩ ።
፳፩	፲፮	፲፱	፴፱	ወይቤልዎ ኢትሰምዕኑ ዘይብሉ ደቂቅ ።
	፪፪	፲፬	፲፮	ዘገብረ ከብካበ ለወልዱ ።
	፫፬	፲፩	፵፮	እስመ የአስሩ ፆረ ከቡደ ።
	፲፪	፲፬	፲፩	እስመ ኵሉ ዘአዕበየ ርእሶ ።
	፲፫	፲፩	፶፪	ለሊከሙ ኢትበውኡ ።
	፳፫		፵፪	አለ ተሐዕብዎ ለጸሕል ወለጽዋዕ ።
	፳፭		፴፱	አለ ታበጥኡ አሥራተ እዴሁ ።
	፳፯		፵፬	አለ ትመስሉ መቃብረ ግብሱሰ ።
	፳፱		፵፯	አለ ተሐንጹ ።
	፴፬		፵፱	ናሁ እፌኑ ኀቤከሙ ።
	፴፯	፲፫	፴፬	ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ።
፳፬	፳፫	፲፯	፳፫	ወለእመ ይቤሉከሙ ነዋ ።
	፳፯		፳፬	እስመ ከመ መብረቅ ።
	፳፰		፴፯	ኀበ ሀሎ ገደላ ።
	፴፯		፳፮	በከመ ኮነ በመዋዕሊሁ ለኖኅ ።
፳፬	፴፱	፲፯	፴	ከማሁ ምጽአቱ ።
	፵		፴፬	አሜሃ ይሄልዉ ፪ቱ ።
	፵፫	፲፪	፴፱	ሶበሁ የአምር በዓለ ቤት ።
	፵፭		፵፪	መኑ እንጋ ገብር ።
	፵፮		፵፫	ብፁዕ ውእቱ ገብር ።
	፵፰		፵፭	ወእመሰ ይቤ ውእቱ ገብር እኩይ ።
፳፭	፲፬	፲፱	፲፫	ፀ ለዘወሀቦ ፭ተ መክሊተ ።
	፳፱		፳፮	እስመ ለዘቦ ይሁብዎ ።

ስድስተኛው ሠንጠረዥ ሁለቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ማርቆስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	
፫	፬	፩	፮	ወልብሱሰ ለዮሐንስ ዘፀጕረ ገመል ።
፬	፲፩		፲፫	ወናሁ መላእክት መጽኡ ።
	፲፱		፲፯	ወይቤሎሙ ንዑ ።
	፳፩		፲፱	ወእዲዎ እምህየ ።
፭	፴	፱	፵፫	እመኒ እዴከ ታስሕተከ ።
፮	፲፬	፲፩	፳፭	ለእመ ኃደግሙ አበሳ ።
፱	፴፮	፮	፴፬	ከመ አባግዕ ዘአልቦ ኖላዊ ።
፲	፲፱	፲፫	፲፩	ሶበ ያገብኡክሙ ።
	፵፪	፱	፵፩	ወዘአስተዮ ለ፩ ጽዋዓ ማይ ቈሪር ።
፲፫	፴፬	፬	፴፬	ወዘእንበለ ምሳሌሰ ኢተናገሮሙ ።
፲፬	፬	፮	፲፰	እስመ ይቤሎ ዮሐንስ ኢይከውነከ ።
	፳፪		፵፭	ወእገበሮሙ ለአርዳኢሁ ።
	፳፭		፵፰	ወበራብዕት ሰዓት ።
፲፭	፪	፯	፫	ኢተሐጽቡ እደዊሆሙ ።
	፲፯		፲፰	ኢለበውክሙኑ ከመ ኵሉ ዘይበውእ ።
	፳፪		፳፭	መጽአት ብእሲት ከነናዊት ።
	፳፰		፳፱	ወይበሎሙ እንስ እማሃል ።
፲፮	፬	፰	፲፪	ወይቤሎሙ ትውልድ ዕሉት ።
	፯		፲፮	እስመ ኅብስተ ኢነሣዕክሙ ።
	፳፪		፴፪	ወእኀዞ ይክልኦ ጴጥሮስ ።
፲፯	፲	፱	፲	ወይቤሉ ጸሐፍት ኤልያስ ይቀድም ።
፲፱	፩	፲	፩	በጽሐ ብሔረ ይሁዳ ።
፳	፳		፴፭	ወመጽአት እሞሙ ።
፳፩	፲፱	፲፩	፲፫	ወረከበ ዕፀ በለስ ።
	፳፩		፳፪	እመ ብክሙ ሃይማኖት ።
፳፪	፴፭	፲፪	፳፰	ወተስእሉ ጸሐፊ ።
፳፬	፲፬	፲፫	፲፩	ወትሰበክ ዛቲ ወንጌል ።
	፲፭		፲፬	እምከመ ርኢክሙ ።
	፳		፲፰	ወጸልዩ ባሕቱ ከመ ኢይኩን ጕየክሙ ።
	፳፪		፳	ሶበ ኢኀጸረ ።
	፳፬		፳፪	እስመ ይመጽኡ ሐሳውያን ።
	፴፮		፴፪	ወበእንተሰ ይእቲ ዕለት ።
	፵፪		፴፭	እስመ ኢተአምሩ ።
፳፮	፳፬	፲፬	፳፩	እምኀየሶ ሰብ ኢተወልደ ።
	፴		፳፮	እንቢቦሙ ወሰቢሖሙ ።
	፴፪		፳፰	ወእምድኅረ ተንሣእኩ እቀድሞሙ ።
	፴፮		፴፪	ወይቤሎሙ ንበሩ ዝየ ።
	፵፪		፴፱	ወካዕበ ሖረ ወጸለየ ።
	፶፮		፶	ወእምዝ ኀደግዎ አርዳኢሁ ።
	፷፭		፷፫	ወሰጠጠ አልባሲሁ ።
፳፯	፳፯	፲፭	፲፮	ወእምዝ ተመጠውዎ ሰገራት ።
	፵፮		፴፬	ወጸርሐ እግዚእ ኢየሱስ ።
	፶፭		፵	ወሀለዋ አንስት ።
	፴፩		፳	ወተማሲቆሙ ሰለብዎ ።
	፴፱		፳፱	ወእለሂ የኀልፉ ይፀርፉ ።

ስድስተኛው ሠንጠረዥ ሁለቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ማርቆስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	
	፲፩		፪	ወይቤሎ አንተ ትቤ ።
	፶፯		፵፪	ወመስዮ መጽአ ብእሲ ።
	፷፩		፵፯	ወሀለዋ አንስትኒ ይቀውማ ።

ሰባተኛው ሠንጠረዥ ሁለቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ዮሐንስ የሚተባበሩበት ።

ማቴዎስ		ዮሐንስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	
፪	፬	፯	፵፪	አይቴ ይትወለድ ክርስቶስ ።
፬	፲፫	፪	፲፪	ወመጺኦ ኀደረ ቅፍርናሆም ።
	፲፪	፬	፫	ወኀደጋ ለምድረ ይሁዳ ።
፲፫	፶፬		፫	ወሖረ ገሊላ ።
	፶፭	፮	፵፪	አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልደ ዮሴፍ ።
፲፰	፲፰	፳	፳፫	ዘአሰርክሙ በምድር ።
፳፩	፭	፲፪	፲፭	ወበልዋ ለወለተ ጽዮን ።

ስምንተኛው ሠንጠረዥ ሁለቱ ወንጌላውያን ማርቆስና ሉቃስ የሚተባበሩበት ።

ማርቆስ		ሉቃስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	
፩	፳፩	፬	፴፩	ወሖረ ቅፍርናሆም ።
	፳፫		፴፬	ምንት ብየ ።
	፴፬		፵፩	ወኢያብሖሙ ይንብቡ ።
	፴፭		፵፪	በጽባሕ ተንሥአ ።
፫	፲፩		፴፫	ጸርሐ እንዘ ይብል ።
	፳፪	፰	፵፩	ወመጽአ ኀቤሁ ኢያኤሮስ ።
	፳		፴፱	ወወፂአ ሰበከ ።
፮	፴፪	፱	፲	ወሖሩ ሐቅለ ።
፯	፴፯	፰	፶፮	ወፈድፋደ ያንከሩ ።
፱	፴፰	፱	፵፱	ቦ ዘርኢነ ፩ደ ።
፲፪	፵	፳	፵፯	እለ ይመኀኑዎን ።
፲፭	፳፰	፳፪	፴፯	ተኈለቈ ።
፲፮	፩	፳፫	፶፮	ወኃሊፎ ሰንበት ።

ዘጠነኛው ሠንጠረዥ ሁለቱ ወንጌላውያን ሉቃስና ዮሐንስ የሚተባበሩበት ።

ሉቃስ		ዮሐንስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	
፭	፬	፳፩	፮	ያወርዱ መሣግሪሆሙ ።
	፮		፲፩	ወሰሐበ መሣግርተ ።
	፭		፫	ስራኅነ ኵላ ሌሊተ ።
፳፪	፫	፲፫	፪	ወቦአ ሰይጣን ውስተ ልቡ ።
	፴፫		፴፯	ወይቤሎ አንስ ጥቡዕ አነ ።
	፴፫	፳፩	፲፭	ተኣምር ከመ አነ አፈቅረከ ።
፳፫	፲፬	፲፰	፴፰	ወአልቦ ዘረከብኩ ኃጢአተ ።
	፬	፲፱	፬	አልቦ ዘረከብኩ አበሳ ።
	፲	፲፰	፲፰	ወይቀውሙ ።
	፳፪	፲፱	፮	ወአልቦ ዘረከብኩ ጌጋየ ።

ዘጠነኛው ሠንጠረዥ ሁለቱ ወንጌላውያን ሉቃስና ዮሐንስ የሚተባበሩበት ።

ሉቃስ		ዮሐንስ		
ም	ቍ	ም	ቍ	
	፲፭		፮	ወአልቦ ዘረከብኩ ጌጋየ ።
	፳፩		፮	ወይቤሉ ስቅሎ ።
፳፬	፲፪	፳፩	፲፩	ወተንሥአ ጴጥሮስ ።
	፲፫	፳	፳፭	ወእንዘ የሐውሩ ፪ቱ ።
	፴፬	፳፩	፯	ወይቤሉ ለጴጥሮስ እግዚእነ ውእቱ ።
	፴፭		፯	እስመ አእመረ ከመ እግዚእነ ።
	፴፮		፲፱	ወዝንቱ ሣልሱ እንዘ ያስተርእዮሙ ።
	፴፯	፳	፳	ወተፈርሁ እርዳኢሁ ።
	፴፮	፳፩	፩	ወእምዝ አስተርእዮሙ ።
	፴፱	፳	፳፯	ርእዩ እደውየ ወእገርየ ።

ዐሥረኛው ሠንጠረዥ አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ የተለያዩበት ።

ማቴዎስ		
ም	ቍ	
፩	፲፯	ወኩሎንኬ ትውልድ ፤
	፲፱	ወዮሴፍሰ ፈኃሪሃ ለማርያም ።
፪	፩	ወናሁ መሰግላን ።
	፱	ወናሁ ኮከብ ።
፫	፲፬	ወይቤ አነ እፈቅድ እጠመቅ ፤
፭	፩	ወርእዮ ብዙኃነ አሕዛበ ።
፮	፩	ዑቁ ኢትግበሩ ምጽዋተክሙ ።
	፲፮	ወሶበሂ ትጸውሙ ።
፯	፮	ኢተሀቡ ቅድሳተ ።
	፲፭	ተዓቀቡ እምሐሳውያን ።
፲	፳፫	ወሶበ ይሰድዱክሙ ።
፲፩	፳	ወእምዝ አኀዘ ይኄሶን ፤
	፳፫	ወአንቲኒ ቅፍርናሆም ፤
	፳፰	ንዑ ኩልክሙ ስሩኃን ።
፲፪	፭	ኢያንበብክሙኑ ዘይቤ ።
	፲፰	ናሁ ቍልዔየ ዘኅረይኩ ።
	፴፫	ወእመ አኮ ግበሩ ዕፀ ሠናየ ፤
	፴፮	ኩሉ ዘነበበ ቃለ ጽሩዓ ፤
፲፫	፳፬	ብእሲ ዘዘርዓ ሠናየ ዘርዓ ።
	፵፬	መድፍን ኀቡእ ።
፲፬	፳፰	እመ አንተሁ እዝዝኒ ፤
፲፭	፲፪	ተአምርሁ ከመ ፈሪሳውያን
፲፮	፲፯	ብፁዕ አንተ ስምዖን ።
፲፯	፲፫	ወአእመሩ ከመ በእንተ ዮሐንስ ።
	፳፬	ወመጽኡ እለ ጸባሕተ ይነሥኡ ።

ማቴዎስ		
ም	ቍ	
፭	፬	ብፁዓን የዋሐን ፤
	፯	ብፁዓን መሐርያን ።
	፲፯	ኢይምሰልክሙ ዘመጻእኩ ።
	፲፱	ዘኬ ፈትሐ ።
	፴፯	ወይኩን ነገርክሙ ።
	፵፩	ወለዘሂ አበ አበጠከ ፩ደ ፤
	፴፪	ፈጽሙ መሥፈርተ አበዊክሙ ።
፳፬	፲	የዓልው ብዙኃን ሃይማኖቶሙ ።
	፳፱	ወእምድኅረ ሕማሞሙ ።
፳፭	፩	አሥሮን ደናግለ ።
	፴፩	ወአመ ይመጽእ ።
፳፮	፳፪	አነኑ እንጋ ።
	፶፪	እለ መጥባሕተ ያነሥኡ ።
	፶፫	ይመስለክሙኑ ዘኢይክል ።
፳፯	፫	ሶበ ርእየ ይሁዳ ።
	፲፱	ለእከት ኀቤሁ ብእሲቱ ።
	፳፬	ነሥአ ማየ ወተሐፅበ ።
	፭	ሖረ ወተሐንቀ ።
	፶፩	ወአድለቅለቀት ምድር ።
	፷፪	ወበሳኒታ እንተ ይእቲ እምድኅረ ዓረብ
፳፰	፱	ወአኀዛ እገሪሁ ወሰገዳ ።
	፲፪	ወወሀብዎሙ ብዙኃ ወርቀ ።

ዐሥረኛው ሠንጠረዥ አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ የተለያዩበት ።

ማቴዎስ የተለየበት ።

ም	ቁ	
፲፰	፲	ዑቁ ኢታስትሐቅርዎሙ ፤
	፲፯	ወለእመ ኢሰምዓከ ።
	፲፱	ለእመ ኅብሩ ፪ቱ ።
	፳፫	ብእሴ ንጉሠ ዘፈቀደ ይግበር ።
፲፱	፲	እመስ ከመዝ ውእቱ ፤
፳	፩	ብእሴ በዓለ ቤት ዘወፅአ በነግህ ።
	፰	ወሶበ መስየ ይቤሎ ለመጋቢሁ ።
፳፩	፲	ወበዊአ ኢየሩሳሌም ተሐውከት ፤
	፲፬	ወእምጽኡ ኅቤሁ ዕውራን ።
	፳፰	ለብእሲ ቦቱ ፪ቱ ደቂቅ ፤
፳፪	፲፩	ወበዊአ ንጉሥ ይርአዮሙ ።
፳፫	፪	ዲበ መንበረ ሙሴ ነበሩ ለክሙ
	፲	ወኢትሰምዩ መምህረ ።
	፲፫	እስመ ተዓፅው ።
	፳፬	እለ ፃጹተ ትነጥፉ ።

ማርቆስ የተለየበት ።

ም	ቁ	
፩	፳፯	እስከ ያንከሩ ።
፫	፲፯	ወሰመዮሙ በእኔርጌስ ።
፬	፳፮	ከመ ብእሲ ዘዘርዓ ።
	፴፰	ወእንቅሕዎ ።
፮	፲፭	ወቦ እለ ይቤሉ ነቢይ ።
	፴፩	ወይቤሎሙ ንዑ ንፃእ ።
፯	፪	ወርእዮሙ ለአርዳኢሁ ።
	፴፩	ወኀሊፎ እምጢሮስ ።
፰	፳፪	ወበጺሖ ቤተ ሳይዳ ።
	፴	ወአዘዞሙ ኢይንግሩ ።
፱	፲፬	ረከበ ብዙኃነ ሰብአ ።
	፳፰	በእፎ ንሕነ ስእነ አውፅኦቶ ።

ማርቆስ የተለየበት ።

ም	ቁ	
፱	፴፫	ምንተኑ ሐለይክሙ ።
	፵፯	ኅበ ዕጼሁ ኢይነውም ።
፲	፲	ወበቤት ካዕበ ተስእልዎ ።
፲፩	፲፱	ወእምከመ መስየ ።
፲፪	፴፪	ሠናየ ትቤ አ ሊቅ ።
፲፬	፶፩	ወተለዎ ፩ዱ ወሬዛ ።
፲፮	፭	ወበዊአን ውስተ መቃብር ።
	፰	ወወፅአ እመቃብር ።
	፲፪	ወእምዝ እንከ እስተርአዮሙ ለ፪ቱ ።

ሉቃስ የተለየበት

ም	ቁ	
፩	፩	እስመ ብዙኃን እለ እኀዙ ።
	፳	ወናሁ ትከውን በሀመ ።
፪	፵፰	ወሶበ ርእይዎ ደንገፁ ፤
፫	፲	ወይቤልዎ ምንተ ንግበር ፤
፬	፲፮	ወሖረ ናዝሬተ ፤
	፳፫	ዓቃቤ ሥራይ ፈውስ ርእሰከ ።
	፳፭	ብዙኃት መበለታት ።

ሉቃስ የተለየበት ።

ም	ቁ	
፲፪	፵፯	ወለገብርሰ ዘየአምር ።
፲፫	፩	እለ ደመረ ጲላጦስ ደሞሙ ።
	፮	ቦቱ በለስ ለብእሲ ።
	፲፬	ወተምዓ መጋቤ ምኵራብ ።
	፲፯	ተኀፍሩ ኵሎሙ ።
	፳፭	ወይትንሣእ በዓለ ቤት ።
	፴፩	ሄሮድስ ይፈቅድ ይቅትልከ ።
፲፬	፪	ብእሲ ቅብው ቅድሜሁ ።
	፯	እስመ ይትባደሩ ።
	፲፪	ወሶበ ትገብር በዓለ ።
	፳፰	ዘይፈቅድ ይሕንጽ ።
፲፭	፰	ዐሥሩ ጠፋልሐ እግሙስ ።
	፲፪	አባ ሀበኒ መክፈልተ ርስትየ ።
፲፮	፩	፩ብእሲ ባዕል ቦቱ መጋቢ ።
	፲፬	ተቃጸብዎ ፈሪሳውያን ።
፳	፩	ነዳይ ዘስሙ አልዓዛር ።
፲፯	፯	ዘቦ ግብር ሐረሳዊ ።
	፳፪	ከመ ትርአዩ መዋዕለ ።
	፳፰	በመዋዕሊሁ ለሎጥ ።
	፴፩	ወዘሂ ገዳመ ሀሎ ።
፲፰	፪	ዘኢይፈርሆ ለእግዚአብሔር ።
	፴፬	እሙንቱስ ኢለበው ።
፲፱	፪	ዘስሙ ዘኬዎስ ፤

ዐሥረኛው ሠንጠረዥ አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ የተለያዩበት ፤

ሉቃስ የተለየበት ፤

ም	ቍ	
፭	፩	እንዘ ያጸምዑ ቃለ እግዚአብሔር ።
	፰	ወርእየ ስምዖን ።
፮	፳፬	አሌ ለክሙ አብዕልት ።
	፳፮	አሌ ለክሙ ሶበ ሠናየ ይብሉክሙ ።
፯	፲፮	ዐቢይ ነቢይ ተንሥአ ።
	፲፰	ወነገርዎ ለዮሐንስ ።
	፳፱	ወተጠምቁ በጥምቀተ ዮሐንስ ።
፲፩	፶፫	ወእኃዙ ያመንዝዝዎ ።
፲፪	፲፫	በሎ ለእኁየ ይክፍለኒ ርስቶ ።
	፴፪	ኢትፍርሁ አ ንኡስ መርዔት ።
	፴፭	ቅኑተ ይኩን ሐቌክሙ ።

ሉቃስ የተለየበት ።

ም	ቍ	
	፲	ይኅሥሥ ወያድኅን ።
	፵፩	ርእያ ለሀገር ወበከየ ላዕሌሃ ።
፳፩	፳	የዓግትዋ ሠራዊት ።
	፳፬	ወይወድቁ በኩናት ።
	፳፭	ወይትመነደቡ አሕዛብ እምድምፀ ባሕር ።
	፴፬	ዑቁ ኢታክብዱ ልበክሙ ።
፳፪	፲፭	ፈቲወ ፈተውክዎ ።
	፳፬	መኑ ውእቱ ዘየዓቢ ።
	፴፩	ናሁ ሰአለ ሰይጣን ።
	፴፭	አመ ፈነውኩክሙ ።
	፴፰	ናሁ ሀለው ፪ቱ መጣብሕ ፤

ሉቃስ የተለየበት

ም	ቍ	
፳፪	፵፫	መልአክ ዘያጽንዖ ፤
	፶፫	ዝንቱ ውእቱ ሰዓትክሙ ፤
	፷፯	እመኒ አይዳእኩክሙ ፤
	፸	አንተኑ ወልደ እግዚአብሔር ፤
፳፫	፮	ተስእለ ገሊላውያን ።
	፲፩	ወአስተአከዮ ሄሮድስ ፤
	፲፫	ወጸውዖሙ ጲላጦስ ፤
	፳፯	ወአንስትኒ ይበክያሁ ፤
	፴	ትብልዎሙ ለአድባር ደቁ ላዕሌነ
	፴፩	በዘ ዕፀ ርጡብ ፤
	፴፬	አባ ኅድግ ሎሙ ፤
	፵	ወገሠጾ ካልኡ ።
	፵፬	ወቀቲሮ ጊዜ ስሱ ሰዓት ሞተ ፀሐይ
	፵፮	ውስተ እዴከ አመኅጽን ነፍስየ
	፵፰	ጐድኡ እንግዳዓቲሆሙ ፤
፳፬	፲፭	ወኮነ ዝንቱ ነገር ክመ ዝንጋዔ ።
	፲፮	ተአኅዘ አዕይንቲሆሙ ፤
	፲፰	ወአውሥአ ፩ዱ ዘስሙ ቀለዮጳ ።
	፵	ወዘንተ ብሂሎ አርአዮሙ ፤
	፵፬	እኮኑ ዝንቱ ነገርየ ዘበአንቲአክሙ

ዮሐንስ የተለየበት

ም	ቍ	
፩	፲፪	ወለአለሰ ተወክፍዎ ።
	፲፮	እስመ እምተረፈ ዚአሁ ።

ዮሐንስ የተለየበት ፤

ም	ቍ	
፪	፲፯	ወተዘከሩ አርዳኢሁ ።
	፲፱	ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ
፫	፳፭	ወእምዝ ኮነ ተኃሥሦ ።
	፳፱	ዘቦቱ መርዓት ።
	፴፮	ዘየአምን በወልድ ።
፬	፭	እንተ ስማ ሲካር ።
	፵፭	ተቀበልዎ ገሊላውያን ።
፭	፲፩	ዘአሕየወኒ ውእቱ ይቤለኒ ።
	፳፬	ዘይሰምዕ ቃልየ ።
	፴፩	እመሰ ለልየ ሰምዓ ኮንኩ ፤
	፵፭	ሀሎ ሙሴ ።
፮	፲፬	ወርእዮሙ ሕዝብ ።
	፳፪	ወባሳኒታ ርእዮሙ ።
	፴፩	አበዊነሰ መና በልዑ
	፴፯	ኵሉ ዘወሀበኒ አቡየ ።
	፴፱	ወዝንቱ ውእቱ ፈቃዱ ።
	፵፬	እሙ ኢሰሐቦ ፤
	፵፯	ዘየአምን ብየ ።
	፵፱	አበዊክሙሰ መናበልዑ በገዳም
	፶፪	ወተዋቀሡ አይሁድ ።
	፶፬	ዘበልዓ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ።
	፷፫	ወዝኒ ቃል ዘነገርኩክሙ ።
	፷፭	አልቦ ዘይክል መጺአ ።
	፸	አኮኑ አነ ዘኅረይኩክሙ ።
፯	፴፩	ብዙኃን እለ አምኑ ቦቱ ።
	፴፫	ዓዲ ኅዳጠ መዋዕለ ሀሎኩ ።
	፴፬	ተኀሥሡኒ ወኢትረክቡኒ ።
	፵	አማን ነቢይ ውእቱ ።

ዐሥረኛው ሠንጠረዥ አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ የተለያዩበት ።

ዮሐንስ የተለየበት ።

ም	ቍ	
	፲፱	ወዝንቱ ውእቱ ስምዑ ።
	፳፬	ወእለሰ ተፈነዉ ።
	፳፰	ወከመዝ ኮነ ።
	፳፱	ንዋ በግዑ ።
	፵፩	ወአቅደመ ረኪበ እኁሁ ።
	፵፫	ወበሳኒታ ፈቀደ ።
፲፪	፲፩	ወብዙኃን እምአይሁድ እለ ሖሩ ።
	፲፮	ወቀዲሙሰ ኢያአመሩ አርዳኢሁ ።
	፳፬	እመ ኢወድቀት ።
	፳፰	ሰባሕኩከኒ ።
	፵	ወበእንተዝ ስዕኑ ።
	፵፪	ወብዙኃን እመላእክተ ሕዝብ እለ እምኑ ቦቱ ።
	፵፬	ወጸርሐ እግዚእ ኢየሱስ ።
፲፫	፩	እምቅድመ በዓለ ፋሲካ ።
	፬	ነሢኦ መክፈ ዘለንጽ ።
	፲፬	ሶበ አነ ሊቅክሙ ።
	፲፰	አኮ በእንተ ኵልክሙ ።
	፳፮	ወጸብሐ ኅብስተ ፤
	፴፮	አይቴኑ ተሐውር እግዚእ ፤
፲፬	፲፫	ወዘሰአልክምዎ ለአብ በስምየ ፤
	፳፭	ወዘንተ ነገርኩክሙ ።
፲፭	፯	ወእመሰ ነበርክሙ ።
	፲፯	ወዘንተ አዘዝኩክሙ ።
	፲፰	እመኒ ዓለም ጸልአክሙ ።
	፳	እምከመ ኪያየ ሰደዱ ፤
	፳፪	ሶበሰ ኢመጻእኩ ወኢነገርክዎሙ ።
	፳፫	ዘጸልዓ ኪያየ ጸልአ ለአቡየ ፤
	፳፬	ወሶበ ኢገበርኩ ሎሙ ፤
፲፮	፬	ወቀዲሙሰ ኢነገርኩክሙ ፤
	፲፬	እምዚአየ ይነሥእ ወይነግረክሙ ።
፲፯	፩	ወዘንተ ነገረ ተናጊሮ ፤
፲፰	፬	ወወፅአ አፍአ ።
	፲	ወቦ መጥባሕት
	፲፫	ወወሰድዎ ኀበ ሐና ቀዳሚ ።

ዮሐንስ የተለየበት

ም	ቍ	
	፵፫	ወተናፈቁ በበይናቲሆሙ ።
	፵፭	ወተሰውጡ ወዓልያኒሆሙ ።
፰	፳፩	አንሰ እሐውር ።
	፳፰	አሚሃ ተአምሩ ከመ አነ ውእቱ።
፲	፵፩	ወብዙኃን ሖሩ ኀቤሁ ።
፲፪	፩	እምቅድመ ሰዱስ መዋዕል ዘፋሲካ ።
	፲፭	ቦአ ዝኩ ረድእ ዘልሙድ ።
	፲፮	ወጴጥሮስሰ ቆመ ።
	፲፮	ወወፅአ ዝኩ ረድእ ።
	፲፱	ወተሰአሎ ሊቀ ካህናት ።
	፳	አንሰ ክሡተ ተናገርኩ ፤
	፳፪	ከመዝኑ ትትዋሥኦ ፤
	፳፬	ወፈነዎ ሐሙዩ ፤
	፳፰	ወኢቦኡ አይሁድ ውስተ ዓውድ
	፴፬	ዘእምልብከኑ ትብል ዘንተ ፤
	፴፯	እንከሰኬ ንጉሥ አንተ ።
	፴፰	ምንትኑ ውእቱ ጽድቅ ፤
፲፱	፯	ንሕነሰ ሕግ ብነ ፤
	፲	ሊተኑ ኢትነብበኒ ፤
	፲፬	ነዋ ንጉሥክሙ ።
	፲፭	አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሣር ።
	፳፭	ወይቀውማ ኀበ መስቀሉ ።
	፳፰	ይቤ ጸማዕኩ ።
	፴፩	ኢይቤታ ዲበ መሳቅሊሆን ።
	፴፱	ወመጽአ ኒቆዲሞስኒ ።
፳	፲	ወአተዉ ቤቶሙ ።
	፳፪	ነፍሐ ላዕሌሆሙ ።
	፳፮	እምድኅረ ሰሙን ዕለት ።
፳፩	፩	በብሔረ ጥብርያዶስ ።
	፱	ወረከቡ ፍሕመ ብቁዐ ።
	፲፪	ንዑ ንምሳሕ ።
	፲፭	ረዓይኬ አባግዕየ ፤
	፲፰	ወአመ ወሬዛ አንተ ።
	፲፰	ወእመሰ ልሕቀ ፤

* * *